አማርኛ መዝገበ ቃላት

ለ ሚ/ር ብሁይ ላንስሌይ

ለዚህ መዝገበ ቃላት ዝግጅት
ላደረጉት አስተዋፅኦ የመዝገበ
ቃላቱን አንድ ቅጅ ከምስጋና
ጋር አበርክተናል።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል
አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የካቲት 1993

መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው

የፊት ሽፋን ስዕል: በአክሱማውያን ዘመን በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ በጥቅም ላይ የዋለውና የኢትዮጵያ የፅህፈት ስርአት መነሻ የሆነው የፊደል ገበታ። (ምንጭ፡ ተሰማ ሃብተ ሚካኤል፥1951። ከሳቴ ብርሃን አማርኛ መዝገበ ቃላት። አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፥ አዲስ አበባ።)

የኋላ ሽፋን ስዕል:- የአማርኛ ቋንቋ በፅሁፌት ላይ መዋል የጀመረበትን ጊዜ ለማወቅ በሚደረገው ጥረት እስካሁን በተገኘው መረጃ መሰረት በ14ኛው ክፍለ ዘመን ለነገሡት ለአፄ አምደፅዮንና ለአፄ ዳዊት፥ እንዲሁም በ15ኛው ክፍለ ዘመን ለነገሠው ለአፄ ይስሃቅ የተገጠሙ የውዳሴ ግጥሞች በከፊል። (ምንጭ፡- ተክለፃዲቅ መኩሪያ፥ 1966። የኢትዮጵያ ታሪክ ከአፄ ይኩኖ አምላክ እስከ አፄ ልብነ ድንግል። ብርሃንና ሰላም ቀ. ሃ. ስ. ማተሚያ ቤት፤ አዲስ አበባ።)

ለመጀመሪያ ጊዜ በ1993 አ. ም. ታተመ።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል፡ 1993። **አማርኛ መዝገበ ቃላት**። አዲስ አበባ፡
አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

መቅድም

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን ለማጥናትና ለእድገታቸው አጋዥ የሆኑ ተግባራትን ለማከናወን የተቋቋመ ተቋም ነው። የማእከሉ መነሻ የነበረው "ብሄራዊ የአማርኛ መርሃ ልሳን ድርጅት" በ1964 በአዋጅ ሲቋቋም የነበረው አላማ የአማርኛ ቋንቋን እድገት መከታተል ነበር። ሆኖም በ1966 የተከሰተውን የስርአት ለውጥ ተከትሎ ማእከሉ "የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ" በሚል ስያሜ አቢይ የሆነ የአላማና የአደረጃጀት ለውጦችን በማድረግ በኢትዮጵያ የሚገኙ ቋንቋዎችን ሁሉ በእኩልነት የሚያገለግል ተቋም እንዲሆን ተደረገ።

አካዳሚው በባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስቴር በኋላም በማስታወቂያና ባህል ሚኒስቴር ስር በነበረባቸው ሁለት አስርታት በአዋጅ የተሰጠ ህልውና ሳይኖረውና በሰው ሃይልና ድርጅታዊ አቅም ሳይጠናከር በልዩ ልዩ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ላይ ጠቃሚ የሆኑ በርካታ የስነልሳን ጥናቶችን ሊያከናውን ችሏል። እንዲሁም የኢትዮጵያን ልዩ ልዩ ብሄሮችና ብሄረሰቦች የስነቃል ሃብት በመሰብሰብ፣ በማጥናትና ደረጃ በደረጃ እያሳተመ ለህዝብ በማቅረብ፣ በልዩ ልዩ ቋንቋዎች ልሳን ክልኤና ልሳን ዋህድ መዝገበ ቃላት በማዘጋጀት፣ ሌሎችም ቋንቋና ስነፅሁፍ ነክ ተግባራትን በማከናወን የተጣለበትን ሃላፊነት ሲወጣ ቆይቷል። ማእከሉ በአዲስ ስያሜና አደረጃጀት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ስር ከተዋቀረ ወዲህም አላማዎቹን ከግብ ለማድረስ ጥረቱን ቀጥሏል።

በዚህ መሰረት እነሆ ይህንን የአማርኛ መዝገበ ቃላት አሳትሞ ለተጠቃሚዎች አቅርቧል። ከዚህ ቀደም በአማርኛ ቋንቋ ልሳን ክልኤና ልሳን ዋህድ መዝገበ ቃላት የተዘጋጁ ቢሆንም ይህ መዝገበ ቃላት በቃላት ምርጫው፣ በቃላት አፈታት ዘዴውና በመጠኑ ከሌሎቹ ቀደምት መዝገበ ቃላት የተለየ ባህርይ አለው። መዝገበ ቃላቱ በዘመናዊ የመዝገበ ቃላት አይነት አከፋፈል "መካከለኛ መዝገበ ቃላት" ተብሎ የሚመደብና በተለይ በሁለተኛና በከፍተኛ ደረጃ የትምህርት እንቅስቃሴ ውስጥ አገልግሎት ሊሰጥ እንደሚችል ሆኖ የተዘጋጀ ነው።

የዚህ መዝገበ ቃላት መታተም በአማርኛ ቋንቋ የእድገት ታሪክ ውስጥ አንድ አቢይ ክንውን እንደሚሆንና በቋንቋው የእድገት ሂደት ውስጥም ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው የታመነ ነው። ምንም እንኳን በስራው አድካሚነትና ውስብስብነት የተነሳ መዝገበ ቃላቱ ከስህተት ፈፅሞ የፀዳ ነው ለማለት ባይቻልም ለበርካታ አመታት በብዙ ባለሙያዎች ሲደከምበት የኖረው ስራ ለህትመት ብርሃን መብቃቱና ለተጠቃሚዎች መድረስ መቻሉ የሚያስደስት ነው። በተጠቃሚዎችና በቋንቋ ባለሙያዎች ፍተሻ የሚገኙ ግድፈቶችን መሰረት በማድረግም ወደፊት የታረመና የተሻሻለ እትም ለማዘጋጀት ተስፋ ተደርጓል።

ሙያው የሚጠይቀውን አድካሚና አስቸጋሪ ስራ በማከናወን ይህን መዝገበ ቃላት በማዘጋጀት ለአያሌ አመታት ለማስኑት አዘጋጆች፣ ስራው በየጊዜው ያጋጠሙት ችግሮች እንዲፈቱ ልዩ ልዩ ርምጃዎችን በመውሰድ ለረዱ ተቋማት፣ ፅህፈት ቤቶችና የስራ ሃላፊዎች፣ በአጠቃላይ ስራው ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ የየበኩላቸውን አስተዋፅኦ ላደረጉ ሁሉ ማእከሉ የላቀ ምስጋናውን ያቀርባል።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል
አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

መግቢያ

አማርኛ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚነገሩት የደቡብዊ ሴም ቋንቋዎች አንዱ ነው፡፡ ቀደም ሲል በኢትዮጵያ ውስጥ የስራ ቋንቋ ሆኖ ያገለግል የነበረውን ግእዝን በመተካት በ10ኛውና በ13ኛው ክፍሳተ ዘመናት መካከል ባለው ጊዜ አማርኛ የስራ ቋንቋ ሆኖ ማገልገል እንደ ጀመረ የተለያዩ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ቧሂላም ከ17ኛው ክፍለ ዘመን ወዲህ በስነፅሁፍ ጭምር እየዳበረ መጥቶ በተለይ ከ19ኛው ክፍለ ዘመን ወዲህ የተሻለ እድገት በማሳየት አሁን ካለበት ደረጃ ደርሷል፡፡

በአሁኑ ጊዜ የአማርኛ ቋንቋ በጎንደር+ በጎጃም+ በወሎና በሰሜን ሸዋ እንዲሁም በአገሪቱ በሚገኙ ዋና ዋና ከተሞች ውስጥ በሚኖረው በአብዛኛው ህዝብ በላፍ መፍቻነት የሚነገር ሲሆን በሌሎቹ የአገሪቱ ክፍሎችም በርካታ ቁጥር ያለው ህዝብ በሁለተኛ ቋንቋነት ይጠቀምበታል፡፡ ቋንቋው ለረዥም አመታት የስራና የትምህርት መስጫ ቋንቋ ሆኖ ሲያገለግል ከመቆየቱ የተነሳ ከሌሎቹ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጋር ሲነፃፀር በስፋት የሚነገር ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

አማርኛ የፅሁፍ ቋንቋ መሆን ከጀመረበት ጊዜ ወዲህ በተለያዩ ምሁራን ልሳነ ክልኤና ልሳነ ዋህድ የሆኑ መዛግብተ ቃላት ተዘጋጅተውለታል፡፡ ከነዚህም መዛግብተ ቃላት ውስጥ አብዛኛዎቹ የተዘጋጁት በውጭ አገር ምሁራን ሲሆን አላማቸው አማርኛን ከውጭ አገር ቋንቋዎች ጋር በማትራጎም ለልዩ ልዩ የትርጉም ስራዎች አመቺ ሁኔታን መፍጠር ነበር፡፡ በዚህም የተነሳ ብዙዎቹ ቀደምት መዛግብተ ቃላት ልሳነ ክልኤ ናቸው፡፡ በ1698 እ.ኤ.አ. በሂዮብ ሉዶልፍ የተዘጋጀው የመጀመሪያው **"አማርኛ-ላቲን መዝገበ ቃላት"** ÷ ከዚያም በ1841 እ.ኤ.አ. በቻርለስ ዊልያም ኢዘንበርግ የተዘጋጀው **እንግሊዝኛ - አማርኛ መዝገበ ቃላት**÷ በ1881 እ.ኤ.አ. በአንቷን ደ'አባዲ የተዘጋጀው **"ፈረንሳይኛ-አማርኛ መዝገበ ቃላት"**÷ በ1901 እ.ኤ.አ. በኢግናቲዮ ግዊዲ የተዘጋጀው **አማርኛ - ኢጣልያንኛ መዝገበ ቃላት** እና እንደገናም በ1917 እ.ኤ.አ. በአ. ቤቪላኳ የተዘጋጀው **ኢጣልያንኛ - አማርኛ መዝገበ ቃላት**÷ በ1910 እ.ኤ.አ. በቻርለስ አርምብሩስተር የተዘጋጀው **እንግሊዝኛ - አማርኛ መዝገበ ቃላት** እና በ1920 እ.ኤ.አ. በዚሁ ኣጥኚ የተዘጋጀው **አማርኛ - እንግሊዝኛ መዝገበ ቃላት**÷ በ1928 እ.ኤ.አ. በሲ. ኤች. ዎከር የተዘጋጀው **እንግሊዝኛ - አማርኛ መዝገበ ቃላት**÷ በ1929 እ.ኤ.አ. በጂ. ቤትማን የተዘጋጀው **አማርኛ - ፈረንሳይኛ / ፈረንሳይኛ- አማርኛ መዝገበ ቃላት**÷

በ1940 እ.ኤ.አ. በኢግናቲዮ ግዊዲ፥ ፍራንቼስኮ ጋሊና እና በኤንሪኮ ቼሩሊ በጋራ ዳብሮ የተዘጋጀው **አማርኛ – ኢጣልያንኛ መዝገበ ቃላት**፥ በ1965 እ.ኤ.አ. በኢማኑኤል ጋንኪንና በከበደ ደስታ የተዘጋጀው **መስኮብኛ – አማርኛ መዝገበ ቃላት** ፥ በ1969 እ.ኤ.አ. በኢማኑኤል ጋንኪን የተዘጋጀው **አማርኛ–መስኮብኛ መዝገበ ቃላት**፥ በ1970 እ.ኤ.አ. በቶሞኮ ሱዙኪ የተዘጋጀው **የጃፓንኛና አማርኛ መዝገበቃላት**፥ በ1976 እ.ኤ.አ. በዎልፍ ሌዝላው የተዘጋጀው **አማርኛ – እንግሊዝኛ እና እንግሊዝኛ – አማርኛ መዝገበቃላት**፥ በዚሁ አጥኚ በ1973 እ.ኤ.አ. የተዘጋጀው **እንግሊዝኛ አማርኛ አውደ አገባባዊ መዝገበቃላት**፥ በ1983 እ.ኤ.አ. በኢማኑኤል ጋንኪን፥ በኢ. ኪዳይቴን እና በኢ. ሚትሮሂና የተዘጋጀው **መስኮብኛ – አማርኛ የተማሪዎች መዝገበ ቃላት**፥ በ1990 በቶማስ ኬን በሁለት ቅፆች የተዘጋጀው **አማርኛ – እንግሊዝኛ መዝገበ ቃላት** ልሳነ ክልኤ ከሆኑት ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው። እንደዚሁም በሗለኞቹ አመታት በአገር ውስጥ በኢትዮጵያውያን የተዘጋጁትና አማርኛን ከውጭ አገር ቋንቋዎች ጋር የሚያተራጉሙ ልሳነ ክልኤ መዛግብተ ቃላትም ከእነዚሁ ወገን ሊመደቡ ይችላሉ። ኢትዮጵያውያንም፥ አልፎ አልፎ ከውጭ አገር ምሁራን ጋር በመተባበር፥ ቁጥራቸው የበዛ ልሳነ ክልኤ መዛግብተ ቃላት አዘጋጅተዋል። ከእነዚህም መካከል በ1969 በመምህራን ማህበር የተዘጋጀው **ተራማጅ መዝገበ ቃላት**፥ በ1978 የተዘጋጀው **አማርኛ – እንግሊዝኛ ማርክሳዊ ሌኒናዊ መዝገበ ቃላት**፥ በ1986 በኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ የተዘጋጀው **አማርኛ – እንግሊዝኛ የሳይንስና ቴክኖሎጂ መዝገበ ቃላት**፥ በ1990 እ.ኤ.አ. በዝድኔክ ፖላቼክ፥ በመላኩ አበበና በታምራት ተሰፋዬ የተዘጋጀው **አጭር ማህበራዊና ፖለቲካዊ እንግሊዝኛ – አማርኛ መዝገበ ቃላት**፥ በ1973 በአምሳሉ አክሊሉና በጂ. ፒ. ሞስባክ የተዘጋጀው **እንግሊዝኛ – አማርኛ መዝገበ ቃላት**፥ በ1979 በአምሳሉ አክሊሉ የተዘጋጀው **አማርኛ – እንግሊዝኛ መዝገበ ቃላት**፥በ1991 በተክለብርሃን ገብረሚካኤልና በጌታቸው ገብረወልድ የተዘጋጀው **የአማርኛና የእንግሊዝኛ ቃላት መግንቢያ**፥ እንዲሁም በ1991 በማሞ ጉደታና በአለማየሁ ግርማ የተዘጋጀው **እንግሊዝኛ – አማርኛ መዝገበ ቃላት** ይገኙበታል። ከእነዚህም በተጨማሪ ሌሎች የውጭ አገር ቋንቋዎችን ከአማርኛ ጋር የሚያተራጉሙ መዛግብተ ቃላት መኖራቸው ይታወቃል።

አማርኛን ከሌሎች የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጋር ለማተራጎም ከተዘጋጁት ውስጥ ደግሞ በ1948 በአለቃ ኪዳነወልድ ክፍሌ የተዘጋጀው **መፅሃፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሃዲስ**፣ በ1948 ዓ በዮሃንስ ገብረ እግዚአብሄር የተዘጋጀው **መዝገበ ቃላት ትግርኛ - አምሃርኛ**፣ በ1982 በአብዱራሀማን ቀራም የተዘጋጀው **ጨቅቲ ክታብ (ሃረሪ - አማርኛ መዝገበ ቃላት)**፣ በ1989 በአበራ ነፋና ሌሎች የተዘጋጀው **አማርኛ ኦሮምኛ መዝገበ ቃላት** እና በ1991 በኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ የተዘጋጀው **ወላይትኛ - አማርኛ መዝገበ ቃላት** ሊጠቀሱ ይችላሉ። የአማርኛ ቋንቋን የተመለከቱ መዝገበ ቃላት ከላይ የተመለከቱት ብቻ ባይሆኑም ቋንቋው በኢትዮጵያ ታሪክና ባህል ውስጥ የሚጫወተውን ሚናና ያለውን ከፍተኛ ድርሻ ለመጠቆም ያህል እነዚህ በቂ ናቸው።

በ20ኛው ምእተ ዓመት አጋማሽ ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያውያን ምሁራን አማርኛ በአማርኛ የሆኑ መዝገበ ቃላት መዘጋጀት ጀመሩ። ከተዘጋጁት መዝገበ ቃላት መካከል ዋና ዋናዎቹ በ1947 በተፈራ ወርቅ አርምዴ የተዘጋጀው **ያማርኛ ስነ ቃላት**፣ በ1951 ዓ. ም በከሳቴ ብርሃን ተሰማ ሃብተሚካኤል ግዕው የተዘጋጀው **ከሳቴ ብርሃን የአማርኛ መዝገበቃላት**፣ በ1957 በመስፍን ልሳኑ የተዘጋጀው **የአማርኛ መፅሄተ ቃላት**፣ በ1967 ዓ. ም. በደስታ ተክለወልድ የተዘጋጀው **አዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት**፣ በ1961 በሊቀ መዘምራን ሞገስ እቁበ እግዚ የተዘጋጀው **አማርኛ በአማርኛ መዝገበ ቃላት**፣ እንዲሁም በ1992 በኢፍሬም አሰፋ ወረደወርቅ የተዘጋጀው **አዲስ የአማርኛ መዝገበቃላት** ናቸው። ከተጠቀሱት መዝገበ ቃላት ከፊሎቹ ባለ ጥቂት ገፆች ወይም የተለየ ደረጃ ያላቸው ሲሆኑ ሌሎች ደግሞ የመደበኛ መዝገበ ቃላት ደረጃ ያላቸው ናቸው። የእነዚህ መዝገበ ቃላት መዘጋጀት ቋንቋው እንዲደረጅና የመደበኛነቱ ደረጃም ከፍ እንዲል ያደረገው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ከመሆኑ ጋር አዘጋጆቹ አድካሚ የሆነውንና ታላቅ ጥንካሬ የሚጠይቀውን የመዝገበ ቃላት ዝግጅት ስራ በግለሰብ ደረጃ ለማከናወን ደፍረው በመነሳት ውጤታማ ለመሆን መብቃታቸው እጅግ የሚያስመሰግናቸው ነው።

አማርኛ ቋንቋ በየጊዜው የቃላት ሃብቱ እየዳበረ መምጣቱ ግልፅ ነው። በተለይ በዘመናዊቷ ኢትዮጵያ ውስጥ የትምህርት መስጫ ቋንቋ ሆኖ ለረጅም ጊዜ መቆየቱ፣ መፃህፍት፣ ጋዜጦች፣ መፅሄቶች ወዘተ. በዚሁ ቋንቋ እየታተሙ መውጣታቸው፣ በአገሪቱ ውስጥ የስራ ቋንቋና የጋራ መግባቢያ ሆኖ ማገልገሉና ከዘመናዊ አስተሳሰብና ቴክኖሎጂ እድገት ጋር እየተዋወቀ መምጣቱ የቃላት እድገቱ ፈጣን እንዲሆን ረድቶታል። በአሁኑ ወቅት ደግሞ ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ አዳዲስ ፅንሰሃሳቦችን የሚገልፁ ቃላት በነዘረው

የቃላት ክምችት ላይ እየተጨመሩ ሲሆኑ ነባር ቃላትም በተጨማሪ ፅንሰሃሳቦች እየዳበሩና የፍቺ ስፋት እየጨመሩ ይገኛሉ።

ከላይ በጥቅሉ ለማሳየት እንደተሞከረው የአማርኛ ቋንቋ አገልግሎቱና የቃላት ሃብት እየሰፋ መምጣት ዘመናዊ መዝገበ ቃላት የማዘጋጀቱን አስፈላጊነት የጎላ በማድረጉ ይህ የአማርኛ መዝገበ ቃላት እንዲዘጋጅ ተደርጓል። ይህ መዝገበ ቃላት ከበፊቶቹ መዛግብተ ቃላት የሚለይባቸው የራሱ የሆኑ ባሕርያት አሉት።

የቀድሞዎቹ መዛግብተ ቃላት የተዘጋጁት በግለሰብ ደረጃ ሲሆን ይህ መዝገበ ቃላት ግን በተቻለ መጠን ቋንቋውን በአፍ መፍቻነት በሚናገሩ፣ ከተለያዩ አካባቢዎች በመጡና የተለያየ የሥራ ልምድ ባላቸው የቋንቋ ባለሙያዎች በቡድን እንዲዘጋጅ ተደርጓል።

በከሳቴ ብርሃን ተሰማ ሃብተሚካኤል **ከሳቴ ብርሃን የአማርኛ መዝገበ ቃላትና** በደስታ ተክለወልድ **አዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት** ውስጥ እንደሚታየው በዚህ መዝገበ ቃላት በቋንቋው ውስጥ ያሉት የእርባታ ቅርፆች በሙሉ ተመዝግበው እንዲፈቱ አልተደረገም። በዚህም ምክንያት የመነሻ ግሱ ከሚኖረው ፍቺ ተጨማሪ ሌላ ፍቺ ወይም ልዩ ሃሳብ የሌላቸው ውልድ ቃላት (የአእማድ ቅርፅ ያላቸው ቃላት) በአብዛኛው አልተፈቱም። ይህንንም አሰራር መከተል ያስፈለገው የመዝገበ ቃላቱ ተጠቃሚ በመነሻ ቃሉ በተሰጠው ፍቺ መሰረት የውልድ አእማድ ቃላቱን ፍቺ መገመት ይችላል በሚል እምነት ነው።

በዚህ መዝገበ ቃላት ውስጥ የተካተቱት ቃላት የተሰበሰቡት ከቀደምት የአማርኛ መዛግብተ ቃላትና ስነፅሁፍ፣ ቋንቋው በስፋት ከሚነገርባቸው አካባቢዎችና ከተለያዩ የሙያ መስኮች ነው። ለመዝገበቃላቱ መነሻ የሆኑት ቃላት የተገኙት ከቀደምት መዛግብተ ቃላት ሲሆን የቀድሞዎቹ ከተዘጋጁበት ዘመን ወዲህ ወደ ቋንቋው የገቡ አዳዲስ ፅንሰሃሳቦችን የሚገልፁ ቃላትን፣ እንዲሁም ነባር ቃላት የያዟቸውን ተጨማሪ ፍቺዎች እንዲያካትት ተደርጓል። ከዚሁ ጋር በተገናኘ ሁኔታ በቀድሞዎቹ መዛግብተ ቃላት ውስጥ የሚገኙና በዛሬው ወቅት ውስጥ እምብዛም የማይዘወተሩ ቃላትና የቃላት ፍቺዎች እንዲዘለሉና በአንፃሩ መዝገበቃላቱ ወቅታዊውን የአማርኛ አጠቃቀም እንዲያሳይ ተደርጓል። ይህ የሆነበት ምክንያት ነባር ቃላቱ ያላቸውን ጠቀሜታ በመዘንጋት ሳይሆን የዚህ መዝገበ ቃላት ደረጃ “መካከለኛ” በመሆኑና ሊይዝ የሚገባው የቃላት ብዛትም የተወሰነ መሆን ስላለበት ነው።

አብዛኛዎቹ ቃላት በአብዛኛዎቹ የቋንቋው ተናጋሪዎች የእለት ተእለት ኑሮ ውስጥ ተደጋግመው የሚሰሙ ናቸው ተብለው የታመነባቸውና በመደበኛነት የሚታወቁት ሲሆኑ ጥቂቶቹ ደግሞ በመጠኑም ቢሆን ከውስን አካባቢ አልፎ ያለ ታዋቂነት ያላቸው ቀበሌኛዎችና ከየሙያ ዘርፉ ተመርጠው የተወሰዱ ቃላት ናቸው። ፍቺዎችም የተሰጡት በተቻለ መጠን

በሚያሻው፡ አጥር ምጥን ባለና ግልፅ በሆኑ አረፍተ ነገሮች፣ ሃረጎች ወይም ቃላት ነው። በተጨማሪም ከቀደሞዎቹ መዝገበ ቃላት ይልቅ በዚህ መዝገበ ቃላት ውስጥ የቃላቱንም ሆነ የፍቺውን የአጠቃቀም ደረጃ የሚያመለክቱ ማብራሪያዎች (ለምሳሌ እንደ ስድብ፣ ፀያፍ፣ ተራ አነጋገር፣ ሃይማኖት፣... የሉ መግለጫዎች) በብዛት እንዲታከሉ ተደርጓል። አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜም ተገቢ የሆኑ ተጨማሪ መረጃዎች እንዲሰጡና ልዩ ልዩም ፍቺዎች በስእሎች፣ በተራ ወይም በምሳሌያዊ አነጋገሮች ተጠናክረው የበለጠ ግልፅ እንዲሆኑ ተደርገዋል። እነዚህ ማብራሪያዎችና አስረጅዎች በተለይ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው አማርኛ ላልሆኑ ሰዎች የቋንቋውን አጠቃቀምና ባህላዊ የአገላለፅ ዘዴዎች በማሳየት ረገድ ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው። በአጠቃላይ መዝገበ ቃላቱ ከ25, 000 በላይ መነሻና ውልድ ቃላት፣ ሃረጎችና ዘይቤአዊ አገላለፆች ይዟል።

በቃላት አሰባሰብና አመዘጋገብ ደረጃ የመዝገበ ቃላቱ ስራ የተጀመረው በ1970 ዓ.ም በህዳር ወር ነበር። ይሁን እንጂ ስራው ብዙም ሳይቀጥል ከሃምሌ ወር 1970 ዓ.ም አንስቶ እስከ መስከረም 1973 ዓ.ም ድረስ ሙሉ በሙሉ ተቋርጦ ከቆየ በኋላ በጥቅምት ወር 1973 ዓ.ም እንደገና እንዲቀጥል ተደረገ። ከዚያም በኋላ ቢሆን ስራው በተለያዩ ምክንያቶች ሲጓተት ቆይቶ መላ ዝግጅቱ፣ ረቂቁን በታይፕ የማፃፉ ስራ ጭምር፣ እስከ ሰኔ 1989 ዓ.ም. ድረስ ሊዘልቅ ችሏል። የዚህ መዝገበ ቃላት ዝግጅት ተጀምሮ እስከ ተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ በስራው ሂደት ላይ በርከት ያሉ ሙያተኞች በተለያየ ጊዜ ተሳትፈውበታል። ከተሳታፊዎቹ ውስጥ በጣም ጥቂቶቹ እስከ ዝግጅቱ ፍፃሜ የዘለቁ ሲሆን አብዛኞዎቹ ግን በተለያየ ምክንያት (በዝውውር፣ የተሻለ ደሞዝ በመፈለግ፣ ስራው አሰልቺና አስቸጋሪ እንደመሆኑ በዚህ አይነት ስራ ላይ መቀጠሉን ባለመሻት፣...) ለተወሰኑ ጊዜ ብቻ እየሰሩ አቋርጠዋል። ያም ሆነ ይህ ለአመታትም ሆነ ለጥቂት ወራት በስራው ላይ በመሳተፍ፣ አነስም በዛም የየበኩላቸውን አስተዋፅኦ ስላደረጉ የሁሉም ተሳታፊዎች ስም ዝርዝር በስራው ላይ ከነበሩበት የጊዜ ሰሌዳና የተሳትፎ አይነት ጋር እንዲመዘገብ ተደርጓል። ዝርዝሩ የሰፈረው በስሞች የፊደል ተራ ቅደም ተከተል መሰረት ነው።

አዘጋጆች

1.	ሃረገወይን ከበደ	ከመስከረም 1975 – ሚያዝያ 1984 ዓ.ም. በመዝገበ ቃላቱ የመጀመሪያ ደረጃ ረቂቅ ዝግጅት፤ እንዲሁም ከግንቦት 1984 – ጥቅምት 1989 ዓ.ም. በመዝገበ ቃላቱ ረቂቅ የአርትኦት ስራ ላይ ተካፋይ በመሆን፡
2.	ልኡልሰገድ አርዓያውን	ከህዳር 1970 – ነሐሴ 1970 ዓ.ም ከቀደምት የአማርኛ መዝገበ ቃላት ቃላትን እየለቀሙ በአርባት አወራረድ ቅደም ተከተል መሰረት ካርድ ላይ በመመዝገብ ስራ ተካፋይ በመሆን፡
3.	መላኩ አበባ	ከሚያዝያ 1970 – ነሐሴ 1970 ዓ.ም. ከተለያዩ ስነፅሁፎች፤ በተለይም ከአንድምታ የትርጓሜ መጻሕፍት፤ ውስጥ ለየት ያለ ፍቺ ትርጉም ያላቸውን ቃላት በመምረጥና ከነአገባባቸው ካርድ ላይ በመመዝገብ፤ ከመስከረም 1973 – ሚያዝያ 1984 ዓ.ም በመዝገበ ቃላቱ የመጀመሪያ ደረጃ ረቂቅ ዝግጅት ስራ ላይ ተካፋይ በመሆንና በተጨማሪም ከግንቦት 1987 – ሰኔ 1989 ዓ.ም. ቡድኑን በማስተባበር፡
4.	መሰለች መልኬ	ከታህሳስ 1978 – መስከረም 1981 ዓ.ም በመዝገበ ቃላቱ የመጀመሪያ ደረጃ ረቂቅ ዝግጅት ላይ ተካፋይ በመሆን፡
5.	መሰረት ተሰፋዬ	ከመስከረም 1976 – ነሐሴ 1976 ዓ.ም በመዝገበ ቃላቱ የመጀመሪያ ደረጃ ረቂቅ ዝግጅት ላይ ተካፋይ በመሆን፡
6.	ሙሉነህ መንግስቱ	ከጥር 1973 – ሚያዝያ 1981 ዓ.ም. በመዝገበ ቃላቱ የመጀመሪያ ደረጃ ረቂቅ ዝግጅት ላይ በመካፈል፤ በተጨማሪም ከግንቦት 1980 – ሰኔ 1981 ዓ.ም ቡድኑን በማስተባበርና የስራው ተካፋይ በመሆን፡
7.	ታምራት ተሰፋዬ	ከመስከረም 1973 – ሚያዝያ 1984 ዓ.ም. በመዝገበ ቃላቱ የመጀመሪያ ደረጃ ረቂቅ ዝግጅት ላይ በመካፈል፤ እንዲሁም ከግንቦት 1984 – ጥቅምት 1989 ዓ.ም. በመዝገበ ቃላቱ ረቂቅ የአርትኦት ስራ ላይ ተካፋይ በመሆን፡

8.	አለሙ ኃይሌ	ከታኅሣሥ 1976 - ሐምሌ 1976 ዓ.ም በመዝገበ ቃላቱ የመጀመሪያ ደረጃ ረቂቅ ዝግጅት ላይ ተካፋይ በመሆን፤
9.	አረጋ በረደድ	ከህዳር 1970 ነሐሴ 1970 ዓ.ም. ከቀደምት የአማርኛ መዝገበ ቃላት ላይ ቃላትን እየለቀሙ በአርቢቱ አወራረድ ቅደም ተከተል መሰረት ካርድ ላይ በመመዝገብ፤ እንዲሁም ከመስከረም 1973 ሰኔ 1980 ዓ.ም. በመዝገበ ቃላቱ የመጀመሪያ ደረጃ ረቂቅ ዝግጅት ወቅት ቡድኑን በማስተባበርና የስራው ተካፋይ በመሆን፤
10.	አበባ ሲራክ	ከጥቅምት 1979 መስከረም 1981 ዓ.ም በመዝገበ ቃላቱ የመጀመሪያ ደረጃ ረቂቅ ዝግጅት ላይ ተካፋይ በመሆን፤ እንዲሁም ከግንቦት 1984 የካቲት 1987 ዓ.ም. በመዝገበ ቃላቱ ረቂቅ የአርትኦት ስራ ላይ ተካፋይ በመሆን፤
11.	አድማሱ ጥሩነህ	ከመስከረም 1978 ሚያዝያ 1984 ዓ.ም. በመዝገበ ቃላቱ የመጀመሪያ ደረጃ ረቂቅ ዝግጅት ላይ ተካፋይ በመሆን፤ እንዲሁም ከግንቦት 1984 - ጥቅምት 1989 ዓ.ም. በመዝገበ ቃላቱ ረቂቅ የአርትኦት ስራ ላይ ተካፋይ በመሆን፤
12.	ዘውዴ አክሊሉ	ከግንቦት 1973 ዓ.ም በሞት እስከተለዩበት እስከ ነሐሴ 1979 ዓ.ም. በመዝገበ ቃላቱ የመጀመሪያ ደረጃ ረቂቅ ዝግጅት ላይ ተካፋይ በመሆን፤
13.	ዳንኤል ኪሮስ	ከመስከረም 1980 ሐምሌ 1981 ዓ.ም. በመዝገበ ቃላቱ የመጀመሪያ ደረጃ ረቂቅ ዝግጅት ላይ ተካፋይ በመሆን፤
14.	ጌታሁን አማረ	ከመስከረም 1976 - ሚያዝያ 1984 ዓ.ም. በመዝገበ ቃላቱ የመጀመሪያ ደረጃ ረቂቅ ዝግጅት ላይ ተካፋይ በመሆን፤ ከግንቦት 1984 ጥር 1985 ዓ.ም. በመዝገበ ቃላቱ ረቂቅ የአርትኦት ስራ ላይ ተካፋይ በመሆን፤
15.	ጌታቸው ዘሩ	ከመስከረም 1980 - ሚያዝያ 1984 ዓ.ም. በመዝገበቃላቱ የመጀመሪያ ደረጃ ረቂቅ ዝግጅት ላይ ተካፋይ በመሆን፤ እንዲሁም ከግንቦት 1984 - ሚያዝያ 1987 ዓ.ም. በመዝገበቃላቱ ረቂቅ የአርትኦት ስራ ላይ ተካፋይ በመሆን፤ በተጨማሪም ከጥር 1987 - ግንቦት 1987 ዓ.ም.

		ቡድኑን በማስተባበር፡
16.	ሚርማ ሃለርያ	ከህዳር 1970 - ነሃሴ 1970 ዓ.ም ከተለያዩ ስነፅሁፎች ላይ ቃላትን ከነአገባባቸው በመልቀምና ካርድ ላይ በመመዝገብ፡
17.	ፈለቀ አለሙ	ከሃምሌ 1987 - ጥር 1988 ዓ.ም በመዝገበ ቃላቱ መጨረሻ ላይ በአባሪነት የሚሰፍሩትን ምእላድ ቃላት በፊደል ተራቸው መሰረት በመመዝገብና የአርትኦት ስራ የተካሄደባቸውን የቃላት ፍቺዎች ካርድ ላይ በመገልበጥ፡
18.	ፈትለወርቅ ዐጌ	ከህዳር 1986 - ሚያዝያ 1988 ዓ.ም በመዝገበ ቃላቱ ረቂቅ የአርትኦት ስራ ላይ ተካፋይ በመሆን፡

አ ማ ካ ሪ

ዶ/ር አምሳሉ አክሊሉ	የመዝገበ ቃላቱን የመጀመሪያ ደረጃ ረቂቅ በማንበብና ጠቃሚ አስተያየቶችን በመስጠት፡

ፀሃፊዎች /ተያቢዎች/

አስካለ ተሾመ
እመቤት መንግስቱ
ዘውዲቱ መንገሻ
የሺመቤት ቱሉ
ፀሃይ ሃብታሙ

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት መዝገበ ቃላቱ በቀድሞው የባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስቴር ስር በነበረው የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዴሚ በሚዘጋጅበት ወቅት በስራው ላይ የተሳተፉ ሲሆኑ አካዴሚው ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተዛውሮ በአዲስ መዋቅር እንዲደራጅ ሲወሰን ረቂቁ በታይፕ ተፅፎ በጥራዞች ተዘጋጅቶ ነበር። በዩኒቨርሲቲው ስር በአዲስ መዋቅር ስራ የጀመረው የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከልም ረቂቁ እንደገና አንድ ወጥ እርምት እንዲካሄድበት፡ በኮምፒዩተር እንዲተየብ፥ የመረጃ ስእሎችን እንዲያከትትና ለህትመት ዝግጁ በሆነ መልክ እንዲቀርብ በማድረግ ስራው ከጥቅምት 1990 እስከ ጥር

1993 እንዲቀጥል አድርጓል። በዚህ ወቅት ቀደም በስራው ላይ ከነበሩት ባለሙያዎች መካከል በማእከሉ ውስጥ የሚገኙት ወ/ት ሃረገወይን ከበደ ብቻ ስለነበሩ ቀሪዎቹን ስራዎች ለማካሄድ ለስራው ቀረቤታ አላቸው ተብለው የታመነባቸውን ሌሎች ባለሙያዎች በመመደብ፣ በስራው በቂ ልምድ ያላቸውን የቀድሞ ባለሙያዎችና ሌሎች የሙያ እገዛ የሚያደርጉ ሰራተኞችን በትርፍ ሰዓት ክፍያ ቀጥሮ በማሰራት መዝገበቃላቱ አሁን በሚገኝበት መልኩ ለህትመት እንዲበቃ ከፍተኛ ጥረት አድርጓል። በዚህ ወቅት በስራው ላይ የተሳተፉት ባለሙያዎች ስም ከተሳትፎአቸው አይነት ጋር በፊደል ተራ ቅደም ተከተል ቀጥሎ ቀርቧል።

1. ሃረገወይን ከበደ	ከጥቅምት 1990 – ሚያዝያ 1992 ዓ.ም. በመዝገበ ቃላቱ ረቂቅ የመጨረሻ ደረጃ የአርትኦት ስራ ላይ ተካፋይ በመሆን፣ ከግንቦት 1991 – ጥር 1993 ዓ. ም. በመዝገበ ቃላቱ የእርማት ንባብና የኮምፒዩተር አርትኦት ስራ ላይ ተሳታፊ በመሆን፣ እንዲሁም ጠቅላላ ስራውን በማስተባበርና ክትትል በማድረግ፣
2. መላኩ አበራ	ከሰኔ 1990 – መስከረም 1991 ዓ.ም. በመዝገበ ቃላቱ ውስጥ ያልተካተቱ ቃላትን ከፅሁፎቸው አዘጋጅቶ በማሟላት፣ ከህዳር 1991 – ሚያዝያ 1992 ዓ.ም. በመዝገበ ቃላቱ ረቂቅ የመጨረሻ ደረጃ የአርትኦትና የእርማት ስራ ላይ ተካፋይ በመሆን፣
3. ሙሉካ መንግስቱ	ከጥቅምት 1992 – ሚያዝያ 1992 ዓ.ም. በመዝገበ ቃላቱ ረቂቅ የመጨረሻ ደረጃ የአርትኦት ስራና የእርማት ንባብ ላይ ተካፋይ በመሆን፣
4. ማርማ ሀንበ	ከጥቅምት – ሃምሌ 1992 ዓ.ም. በመዝገበ ቃላቱ ረቂቅ የመጨረሻ ደረጃ የአርትኦት ስራ፣ በእርማት ንባብና በኮምፒዩተር አርትኦት ስራ ላይ ተካፋይ በመሆን፣ እንዲሁም ከጥቅምት 1993 – ጥር 1993 ዓ. ም. አጠቃላይ የስራ ሂደቱን በመከታተልና ሌሎች ቴክኒካዊ ድጋፎችን በመስጠት።

በእርምት ንባብ ላይ የተሳተፉ

1. ኃይለየሱስ እንግዳሸት(ዶ/ር)፡	ታህሳስ 1992 ዓ.ም በመዝገበ ቃላቱ የእርምት ንባብ ላይ ተካፋይ በመሆን፡
2. ሳሙኤል ኃይሉ	ከታህሳስ 1992 መጋቢት 1992 ዓ.ም በመዝገበ ቃላቱ የእርምት ንባብ ላይ ተካፋይ በመሆንና በሌሎች ከስራው ጋር ተዛማጅ በሆኑ ቴክኒካዊ ተግባሮች ላይ ተካፋይ በመሆን፡
3. ስርግው ገላው	ታህሳስ 1992 ዓ.ም. በመዝገበ ቃላቱ የእርምት ንባብ ላይ ተካፋይ በመሆን፡
4. አድማሱ ጥሩነህ	ከህዳር 1992 ጥር 1992 ዓ.ም. በመዝገበቃላቱ የእርምት ንባብ ላይ ተካፋይ በመሆን፡

ኮምፒዩተር ፅሁፈት

አምለሰት በላይ	እመቤት መንግስቱ
አስራት ብርቃየሁ	ፅጌረዳ ታደሰ
አስካለ ተሾመ	

ቴክኒካዊ ስራዎች

የመዝገበ ቃላቱ የቅርፅ ዝግጅት፡	ፅጌረዳ ታደሰ
ስእላዊ መግለጫዎች(በከፊል) ፡	ሰላማዊት አበበ

በመጨረሻም ይህ መዝገበቃላት ለህትመት እንዲበቃ ሙያዊና ቴክኒካዊ ርዳታቸውን ለለገሱን፡ በሃሳብ ለረዱንና ላበረታቱን ሁሉ ከፍ ያለ ምስጋና እናቀርባለን። ስራው ተጀምሮ ለረጅም አመታት በቆየበት ጊዜ በተለያየ ደረጃ አስተዋፅኦ ላደረጉ የቀድሞው የባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስቴር የስራ ሃላፊዎች፡ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ ጉባኤ፣ የአካዴሚው የስራ ሃላፊዎችና ሙያተኞች በሙሉ ምስጋናችንን ይድረሳቸው። በተለይም አካዴሚው ወደ ዩኒቨርስቲ ከተዛወረ በሗላ የስራው ሂደት እንዳይደናቀፍ ብርቱ ጥረትና

ክትትል ላደረጉልን የቀድሞው የማእከሉ ሃላፊ ለፕሮፌሰር ባዬ ይማም፤ በአርትኦታቸው እገዛ በመከታተል ስራውን ዳር በማድረስ ረገድም ሆነ በስራው ላይ የሰጡላቸውን አገዛ በማድረግ ለምግር ብርቱ ጥረት ላደረጉት የማእከሉ ሃላፊ ለዶ/ር [illegible] እንግዳሸት ምስጋናችን የላቀ ነው። እንዲሁም በሙሉ ሊቃውንት የመዝገበ ቃላቱን የመጨረሻ ረቂቅ በማንበብ ጠቃሚ የእርምት አስተያየታቸውን ለሰጡን ለአቶ አስፋው ዳምጤ ከፍተኛ ምስጋናችን ይድረሳቸው።

አዘጋጆቹ

ልዩ ማስታወሻ

የዚህ መዝገበ ቃላት ስራ ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ተጠናቀቀበት ድረስ በልዩ ልዩ ደረጃ በስራው ሲሳተፉ ከነበሩት መካከል የሚከተሉት የስራቸውን ውጤት ሳያዩ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል።

1. ዘውዴ አክሊሉ
2. አረጋ በረደድ
3. ታምራት ተሰፋዬ

በተለይ አቶ ታምራት ተሰፋዬ ከትምህርት ቤት ከወጡ ጀምሮ ህይወታቸው እስካለፈበት ጊዜ ድረስ አብዛኛውን የስራ ዘመናቸውን በዚህ መዝገበ ቃላት ስራ ላይ ያዋሉ ናቸው። መዝገበ ቃላቱ ከዚህ ደረጃ እንዲደርስም የነበራቸው ድርሻ፣ ፍቅራቸው የሙያ ፍላጎትና ትጋት ከፍተኛ ነበር።

የፊደል አጠቃቀም

1. በአገልግሎት ላይ ያለው ነባር የፊደል ገበታ

ሀ	ሁ	ሂ	ሃ	ሄ	ህ	ሆ
ለ	ሉ	ሊ	ላ	ሌ	ል	ሎ
ሐ	ሑ	ሒ	ሓ	ሔ	ሕ	ሖ
መ	ሙ	ሚ	ማ	ሜ	ም	ሞ
ሠ	ሡ	ሢ	ሣ	ሤ	ሥ	ሦ
ረ	ሩ	ሪ	ራ	ሬ	ር	ሮ
ሰ	ሱ	ሲ	ሳ	ሴ	ስ	ሶ
ሸ	ሹ	ሺ	ሻ	ሼ	ሽ	ሾ
ቀ	ቁ	ቂ	ቃ	ቄ	ቅ	ቆ
በ	ቡ	ቢ	ባ	ቤ	ብ	ቦ
ተ	ቱ	ቲ	ታ	ቴ	ት	ቶ
ቸ	ቹ	ቺ	ቻ	ቼ	ች	ቾ
ኀ	ኁ	ኂ	ኃ	ኄ	ኅ	ኆ
ነ	ኑ	ኒ	ና	ኔ	ን	ኖ
ኘ	ኙ	ኚ	ኛ	ኜ	ኝ	ኞ
አ	ኡ	ኢ	ኣ	ኤ	እ	ኦ
ከ	ኩ	ኪ	ካ	ኬ	ክ	ኮ
ኸ	ኹ	ኺ	ኻ	ኼ	ኽ	ኾ
ወ	ዉ	ዊ	ዋ	ዌ	ው	ዎ
ዐ	ዑ	ዒ	ዓ	ዔ	ዕ	ዖ
ዘ	ዙ	ዚ	ዛ	ዜ	ዝ	ዞ
ዠ	ዡ	ዢ	ዣ	ዤ	ዥ	ዦ
የ	ዩ	ዪ	ያ	ዬ	ይ	ዮ
ደ	ዱ	ዲ	ዳ	ዴ	ድ	ዶ
ጀ	ጁ	ጂ	ጃ	ጄ	ጅ	ጆ
ገ	ጉ	ጊ	ጋ	ጌ	ግ	ጎ
ጠ	ጡ	ጢ	ጣ	ጤ	ጥ	ጦ
ጨ	ጩ	ጪ	ጫ	ጬ	ጭ	ጮ
ጰ	ጱ	ጲ	ጳ	ጴ	ጵ	ጶ
ጸ	ጹ	ጺ	ጻ	ጼ	ጽ	ጾ
ፀ	ፁ	ፂ	ፃ	ፄ	ፅ	ፆ
ፈ	ፉ	ፊ	ፋ	ፌ	ፍ	ፎ
ፐ	ፑ	ፒ	ፓ	ፔ	ፕ	ፖ
ቨ	ቩ	ቪ	ቫ	ቬ	ቭ	ቮ
ኧ	?	?	?	?	?	?

ዘመን አመጣሽ ፍንፅቆች

ሏ ሟ ሧ ሯ ሷ ሿ ቧ ቯ ቷ ቿ ኗ ኟ ዟ ዧ ዷ ጇ ጧ ጯ ጿ ፏ

ነባር ፍንፅቆች (ህፁፃን/ ዲቃሎች) ተብለው የሚጠሩ ፊደላት

ቈ	ቍ	ቊ	ቋ	ቌ
ኈ	ኍ	ኊ	ኋ	ኌ
ኰ	ኵ	ኲ	ኳ	ኴ
ጐ	ጕ	ጒ	ጓ	ጔ

2. ይህ መዝገበ ቃላት የተዘጋጀበት አዲስ የፊደል ገበታ

በአገልግሎት ላይ ያለው የፊደል ገበታ ከላይ የተመለከተው ቢሆንም ይህ መዝገበቃላት የተዘጋጀበት የፊደል ገበታ ግን የተደገፈው የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ ጉባኤ ያሳለፈውን ውሳኔና መመሪያ ተግባራዊ በማድረግ ከዚህ በታች በሚገኘው የፊደል ገበታ መሰረት ነው።

ሀ	ሁ	ሂ	ሃ	ሄ	ህ	ሆ
ለ	ሉ	ሊ	ላ	ሌ	ል	ሎ
መ	ሙ	ሚ	ማ	ሜ	ም	ሞ
ረ	ሩ	ሪ	ራ	ሬ	ር	ሮ
ሰ	ሱ	ሲ	ሳ	ሴ	ስ	ሶ
ሸ	ሹ	ሺ	ሻ	ሼ	ሽ	ሾ
ቀ	ቁ	ቂ	ቃ	ቄ	ቅ	ቆ
በ	ቡ	ቢ	ባ	ቤ	ብ	ቦ
ቨ	ቩ	ቪ	ቫ	ቬ	ቭ	ቮ
ተ	ቱ	ቲ	ታ	ቴ	ት	ቶ
ቸ	ቹ	ቺ	ቻ	ቼ	ች	ቾ
ነ	ኑ	ኒ	ና	ኔ	ን	ኖ
ኘ	ኙ	ኚ	ኛ	ኜ	ኝ	ኞ
አ	ኡ	ኢ	ኣ	ኤ	እ	ኦ

ከ	ኩ	ኪ	ካ	ኬ	ክ	ኮ
ወ	ዉ	ዊ	ዋ	ዌ	ው	ዎ
ዘ	ዙ	ዚ	ዛ	ዜ	ዝ	ዞ
ዠ	ዡ	ዢ	ዣ	ዤ	ዥ	ዦ
የ	ዩ	ዪ	ያ	ዬ	ይ	ዮ
ደ	ዱ	ዲ	ዳ	ዴ	ድ	ዶ
ጀ	ጁ	ጂ	ጃ	ጄ	ጅ	ጆ
ገ	ጉ	ጊ	ጋ	ጌ	ግ	ጎ
ጠ	ጡ	ጢ	ጣ	ጤ	ጥ	ጦ
ጨ	ጩ	ጪ	ጫ	ጬ	ጭ	ጮ
ጸ	ጹ	ጺ	ጻ	ጼ	ጽ	ጾ
ፀ	ፁ	ፂ	ፃ	ፄ	ፅ	ፆ
ፈ	ፉ	ፊ	ፋ	ፌ	ፍ	ፎ
ፐ	ፑ	ፒ	ፓ	ፔ	ፕ	ፖ

ፍንፅቆች

ሗ ሏ ሟ ሯ ሷ ሿ ቋ ቧ ቷ ቿ ኗ ኟ ኳ ዟ ዧ ዷ ጇ ጓ ጧ ጯ ጿ ፏ

ከዚህ በላይ ባለው የፊደል ገበታ እንደሚታየው በቀድሞው የፊደል ገበታ ተመሳሳይ ድምፅ ካላቸው ሞክሼ ፊደላት መካከል በዚህ መዝገበቃላት ውስጥ የተጠቀምንባቸው ሀ፥ ሰ፥ አ እና ፀ ብቻ ናቸው። ስለዚህ በቀደሞው የፊደል ገበታ ይገኙ የነበሩና የነዚህ ፊደላት ሞክሼ የሆኑ ፊደላት በዚህ መዝገበ ቃላት ውስጥ አልተሰራባቸውም። በተጨማሪ 'ሀ' በራብእ ድምፅ 'ሃ' እየተባለ መጠራቱ ቀርቶ በግእዝ ድምፅ 'ኸ' እየተባለ እንዲጠራ (ለምሳሌ በቀደሞው አፃፃፍ ይኸው ተብሎ በሚፃፈው ምትክ ይሀው ተብሎ እንዲፃፍና 'ሀ' በ 'ኸ' ድምፅ እየተተካ እንዲነበብ) ተደርጓል። በተመሳሳይ መንገድ 'አ' በራብእ ድምፅ 'ኣ' እየተባለ መጠራቱ ቀርቶ በ 'ኧ' ድምፅ እንዲጠራና የ'ኧ' ን ቦታ እየተካ እንዲነበብ (ለምሳሌ ኧረ በሚለው ምትክ አረ ተብሎ እንዲፃፍና 'አ' በ 'ኧ' ድምፅ እንዲጠራ ወይም እንዲነበብ) ተደርጓል። ስለሆነም 'ኧ' ፥ 'ኸ' እና ቀደም ሲል የጠቀስናቸው ሞክሼ ሆሄያት ከነዝርያቸው በዚህ መዝገበቃላት ውስጥ ጥቅም ላይ ኣልዋሉም።

እንደ ሏ፥ ሟ፥ ሯ፥... ሁሉ ቀድሞ ከነበሩት የፍንፅቅ ፊደላት ዘሮች መካከልም የተጠቀምንባቸው ቋ፥ ኳ፥ ጓ የተባሉትን ብቻ ነው። እንደ ቈ፥ ቊ፥ ኰ፥ ኵ፥ ...ያሉት የፍንፅቅ ፊደላት ዘሮች በተቀራራቢ ወይም በተወራራሽ ድምፆች እንዲተኩ ተደርጓል።

በዚህም መሰረት፡

'ቈ' በ 'ቆ' ፡ 'ቋ' በ 'ቃ' ተተክተዋል።
'ኰ' በ 'ኮ' ፡ 'ኳ' በ 'ካ' "
'ጐ' በ 'ጎ' ፡ 'ጓ' በ 'ጋ' "
'ኈ' በ 'ሆ' ፡ 'ኋ' በ 'ሃ' "

በተጨማሪም በ 'ኗ' ቦታ 'ኟ' እንዲተካ ተደርጓል። በአዲሱ የፊደል ገበታ 'ሸ' ከ 'ሰ' ፊደል ዘር ቀጥሎ የተዛፈበት ምክንያት 'ሰ' እና 'ሸ' የቅርፅና የድምፅ ተቀራራቢነት ስላላቸው ተከታትለው ቢቀመጡ ተገቢና አመቺ ሆኖ ስለተገኘ ነው። ምንም እንኳ ይህ መዝገበ ቃላት በአዲሱ የፊደል ገበታ መሰረት ከላይ የተጠቀሱትን ለውጦች ጠብቆ የተዘጋጀ ቢሆንም በአዘጋጆቹም ሆነ በተየቢዎቹ ዘንድ የቀድሞው ፊደል አጠቃቀም ተለምዶ በመኖሩ አልፎ አልፎ ግድፈቶች ሊኖሩ እንደሚችሉ ግልፅ ነው። ስለሆነም ተጠቃሚው ይህንን ሁኔታ ከግምት ውስጥ እንዲያስገባልን እናሳስባለን።

የስርአተ ነጥብ አጠቃቀም

በዚህ መዝገበቃላት ውስጥ ስራ ላይ የዋሉ ስርአተ ነጥቦችና የተለያዩ ምልክቶች፡

1. አንድ ነጥብ /./

ሀ. በአጭሩ የተፃፈን ቃል ያመለክታል።

ምሳሌ፡

ሳይ. — ሳይንስ

ለ. ከአንድ በላይ ፍቺ በሚሰጥበት ሁኔታ ከአሃዝ በኋላ በመቀመጥ አሃዙን ከፍቺዎች ለመለየት ያገለግላል።

ምሳሌ፡-

ማንበር (ማምበር) ስ 1. ወንበር ከተቀመጠበት የራስ ክፍል በታች ከእግር በላይ ያለ የሰውነት ክፍል። 2. ፊት ለፊት። *ቤቱ ማንበር ላይ ነው ያለው።* 3.(ዘይ.) እድል፣ ገድ። *ጥሩ ማንበር አለው።*

2. ሰያፍ መስመር ወይም ህዝባር (/)

ሀ. ረዘም ያለ ቃልን ወይም ሃረግን ለማሳጠር ያገለግላል።

ምሳሌ፡

ት/ሚ   ትምህርት ሚኒስቴር

ለ. አንድን ሃሳብ የሚወክሉ ወይም የሚገልፁ የተለያዩ ቃላት ሲኖሩ ወይም አንድን ፍቺ ለማብራራት የሚያደረደሩ የተለያዩ አስረጂዎች ሲኖሩ ወይም አንዱን ቃል የሚተካው ሌላ ቃል ካለ ተተኪው ወይም አማራጩ ቃል ወይም አስረጅ በሰያፍ መስመር እየተለየ ይቀመጣል።

ምሳሌ፡

ሆዱ አረረ /ቆሰለ/ ተቃጠለ ተናደደ።

3. የኮከብ ምልክት / * /

ፍቺ ወይም ትርጉም ባልተሰጣቸው ቃላት አናት ላይ በስተግራ በኩል ይቀመጣል። እንደነዚህ ያሉት ቃላት በስፋት የማይታወቁ ወይም በአገልግሎት ላይ የሌሉ ወይም ለውልድ ቃላት መነሻ ናቸው ተብለው የግምት ቅርፅ የተሰጣቸው ቃላት ናቸው።

ምሳሌ፡

***ወለበ**

ወለባ ቅ ቀትረ ቀሊል፡ ነጠላ፡ ሾላካ፡ ጥላ ቢስ ።

ውልብ አለ ግ ታይቶ ጠፋ፡ ከመቅፅበት ሽው ብሎ አለፈ ።

4. የጥቅስ ምልክት / "   " /

ከሌላ ሰው እንዳለ የተወሰደ ገለፃን ወይም አረፍተ ነገርን ወይም በተመልካች ጊዜ (በማጣቀስ ጊዜ) የሚተኮሩባቸውን ቃላት ለማመልከት ያገለግላል። እንዲሁም አልፎ አልፎ በፍቺ ውስጥ የሚጠቆሙን አማራጭ ቃል ለይቶ ለማመልከት ያገለግላል።

ምሳሌ፡-

ቡሆ "በካ" ስር "ቡኮ"ን ተመ.

ተርጓሚ ስ 1. በአንድ ቋንቋ የተነገረውን ቋንቋውን ለማያውቅ ሌላ አድማጭ የሚተረጉም፡ "ትርጁማን"ም ይባላል።

5. ሰረዝ / - /

ሀ. አንድ ከፊል ቃል ወይም ምእላድ ወይም ያልተሟላ ቃል ሲኖር ከቃሉ ቀድሞ ወይም ቀጥሎ ከጎኑ በመቀመጥ ያ ቃል ከሌላ ቃል ጋር የሚጣመር መሆኑን ለመጠቆም ያገለግላል።

ምሳሌ፡

ስነ-

በረ-

ነክ

አስተኔ

6. ነጥብጣብ / ... /

በመዘርዘር ገለፃ ጊዜ ሁሉንም ነገሮች ከመጻፍ ይልቅ የተወሰኑትን ብቻ ጠቅሶ ሌሎችንም እንዳሉ ለመጠቆም ይገባል።

ምሳሌ፡

ወለድ አግድ ስ. አበዳሪዎች በገንዘብ ትርፍ ወይም አራጣ ፋንታ የተበዳሪን ቤት፣ መሬት... በመያዣ የሚጠቀሙበት የብድር ውል አይነት ።

7. አራት ማእዘን ቅንፍ / [ ] /

በተናጠል ወይም ከሌላ ቃል ወይም ምእላድ ጋር በመጣመር የሚነገር ቃል ሲኖርና ቃሉ (ያልተጣመረው) ብቻውንም መነገር የሚችል መሆኑን ለማሳየት ሲፈለግ ተጣማሪው ቃል በአራት ማእዘን ቅንፍ ውስጥ ይቀመጣል።

ምሳሌ፡

ቁምጣ [ሱሪ]

ሽሩ [ኤሺማ]

[የ] ብርድ ልብስ

8. ቅንፍ / ( ) /

ሀ. በተለያዩ ቅርፅ ወይም አጠራር የሚነገር ስም ሲያጋጥም እንደመደበኛ የሚቆጠረው ወይም አንደኛው ቃል ብቻ ከቅንፍ ውጪ ሆኖ ሌላው ቃል በቅንፍ ውስጥ ይቀመጣል።

ምሳሌ፡-

ቢላ (ቢላዋ ፥ ቢላዎ)

ቀዥቃዣ (ቀዠቀዥ)

ሁልጊዜ (ሁሌ)

ሙቀጫ (ሙገጫ)

ሰ. ለየት ያለ የብዙ ቁጥር ቅርፅ ያላቸው ቃላት ካሉ የብዙ ቁጥሩ አንዳንዴም የነጠላ ቁጥሩ ቅርፅ በቅንፍ ውስጥ ይቀመጣል።

ምሳሌ፡-

ካህን (ብ.ቁ. ካህናት)

ህፃን (ብ. ቁ. ህፃናት)

ልኡል (ብ. ቁ. ልኡላን)

መኳንንት (ነጠ. ቁ. መኮንን)

ሠ. የሚፈቱት ቃላት ተጨማሪ መግለጫ የሚያስፈልጋቸው ሆኖ ሲገኝ ከቃላቱ ፍቺ በፊት መግለጫው በምህፃረ ቃል ወይም ሙሉ ቃሉ እንዳለ በቅንፍ ይቀመጣል።

ምሳሌ፡-

ሰብሳቢ ቅ (የአራዳ አነ.) ጠጪ፣ ሰካራም።

በሊቃጣ ቅ (ነውር፥ ስድብ) 1. ሃፍረተ ስጋዋ እንዳይታይባት ጥንቃቄ የማታደርግ፣ በርጋዳ። 2. ስነስርአት የሌላት፥...።

ነነዌ (ነይ ነይ) ስ (ኢ. አ. ተ. ቤ.) ከሁዳዴ ፆም መባቻ አስራ አራት...።

ረ. የተሰጡት ፍቺዎች ተጨማሪ መግለጫ ወይም ማብራሪያ የሚያስፈልጋቸው ሆኖ ሲገኝ ከፍቺው በፊት፥ በፍቺው መካከል ወይም ከፍቺው በኋላ መግለጫው ወይም ማብራሪያው በቅንፍ ውስጥ እንዲቀመጥ ይደረጋል።

ምሳሌ፡

ባዶ ቤት ስ 1. ምንም ነገር (ምግብ፥ መጠጥ፣ ገንዘብ፣ ...) የሌለበት ቤት።

2. ሰው የሌለበት ወና ቤት።

በረራ ስ ጉዞ (የአውሮፕላን)።

ተቻቻለ ግ 1. (ክፍያ፥ ወጪ፣ ኪሳራ፥ እዳ፣...) ተጣጣ፥ ተብቃቃ፥ ተካካሰ።

9. ነጠላ ሰረዝ / ፣ / የተለያዩ ነገሮችን ለመዘርዘር ያገለግላል።

ምሳሌ፡-

ተገለለ → ተለየ፥ ተነጠለ፥ ብቸኛ ሆነ፡... ።

10. ድርብ ሰረዝ / ፤ /

ሀ. አረፍተ ነገር አከል በሆኑ ሃሳቦች መካከል ይገባል።

ምሳሌ ፡-

እንተበተበ → እሳት በደንብ ሳይገባውና እስኪንጣጣ ድረስ ብቻ ቆላ፤ በደንብ ሳያበስል አመሰ።

ለ. በቃላት ፍቺ ውስጥ ወይም በፍቺዎች መካከል መጠነኛ የሆነ ልዩነት ሲኖርና በአንድ ቁጥር የፍቺ ሃሳብ ውስጥ የማይጠቃለሉ ግን ደግሞ በሌላ ቁጥር ተለይተው ሳይሆን በዚያው በአንደኛው ቁጥር ውስጥ እንደ ሁለተኛ ፍቺ ሆነው የሚቀርቡ የፍቺ ሃሳቦችን ለመለየት ያገለግላል። እንዲሁም የአንድ ቃል ፍቺ ከተሰጠ በኋላ፥ ተፈቺው ቃል ሌላ ሁለተኛ መጠሪያ ካለው ሁለተኛ ስሙ ወይም መጠሪያው ከፍቺው ቀጥሎ ከድርብ ሰረዝ በኋላ ይቀመጣል ።

ምሳሌ ፡-

ተበላለጠ → 1. አለመጣጠን ወይም እኩል አልሆን አለ፤ ተዛነፈ።

ተዛነብ ለ ከግድግዳ ውጪ ዙሪያውን የሚገኝ፥ ዝናብ ግድግዳን እንዳይጎዳ ለማድረግ የሚያገለግል የጣራ ክፍል፤ ታዛ፤ ሰበሰብ።

11. አራት ነጥብ / ። / በያንዳንዱ አረፍተነገርና በቃል ፍቺ መጨረሻ ላይ ይገኛል።

12. የማጥበቂያ ምልክት / ¨ / አንዳንድ ቃላት የተዋቀሩባቸው ፊደላት ጠብቀው ወይም ላልተው ሲነበቡ የትርጉም ለውጥ የሚያስከትሉ ሲሆኑ ይህንን ለመለየት በሚጠብቀው ፊደል ራስጌ ሁለት ነጥቦች እንዲቀመጥ ተደርጓል።

ምሳሌ ፡-

አሳማ̈ → እንዲታማ አደረገ፥ ምክንያት ሆነ።

ገና ተው. → ወደፊት እንጂ አሁን ያልሆነን፡ ያልተፈፀመን ድርጊት ለማሳየት የሚያገለግል ቃል። *ምሳዬን ገና አልበላሁም* /ሁለተኛ ደረጃን ገና አልጨረሰም።

ገና ስ 1. በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ ታህሳስ 29 ወይም በየአራት አመቱ በዘመነ ዮሃንስ ብቻ ታህሳስ 28 ቀን የሚከበር፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደበት ቀን፤ ልደት፡፡ 2. የገና ጨዋታ፡፡

የምህፃረ ቃላት ዝርዝር

ሙሉ ቃል	አህፅሮት
ሂሳብ	ሂሳ.
ሃይማኖት	ሃይ.
መስተዋድድ	መዋ.
መስተፃምር	መፃ.
መጠይቃዊ ቅፅል	መጠ. ቅ.
መጠይቃዊ ተውላጠ ስም	መጠ. ተው. ስ.
መፅሃፍ ቅዱስ	መ. ቅ.
ማስዘቢያ አነጋገር	ማ. አነ.
ምርቃት	ምር.
ምሳሌ	ምሳ.
ምሳሌያዊ አነጋገር	ምሳ. አነ.
ምእላድ	ምእ.
ሰዋስው	ሰዋ.
ሳይንስ	ሳይ.
ስም	ስ
ስነልሳን	ስነ. ል.
ስነፅሁፍ	ስነ ፅ.
ስፖርት	ስፖ.
ቃለ አጋኖ	ቃ. አ.
ቅፅል	ቅ
ቤተክህነት	ቤ. ክህ.
ብዙ ቁጥር	ብ. ቁ.
ተመልከት	ተመ.
ተራ አነጋገር	ተራ አነ.
ተባእታይ ፆታ	ተባ. ፆ.
ተውላጠ ስም	ተው. ስ.
ተውሳከ ግስ	ተው. ግ.
ትእዛዝ አንቀፅ	ትእ. አን.
ነጠላ ቁጥር	ነጠ. ቁ

ኢኮኖሚ	ኢኮ.
አንስታይ ፆታ	አን. ፆ.
አፍራሽ	አፍ.
እርግማን	እር.
እስልምና ሃይማኖት	እስል.
ኬሚስትሪ	ኬሚ.
ክርስትና ሃይማኖት	ክር.
ዘይቤያዊ	ዘይ.
ዝኒ ከማሁ /ይህም እንደ ላይኛው ነው/	ዝ. ከ.
የማንኳሰስ አጠራር	የማ. አጠ.
የንቀት አነጋገር	የን. አነ.
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን	ኢ. ኦ. ተ. ቤ.
የጊዜ ተውሳከ ግስ	የጊ . ተው. ግ.
ያራዳ(የአራዳ) አነጋገር	ያራዳ(የአራዳ) አነ.
ግስ	ግ
ግብርና	ግብ.
ፍልስፍና	ፍል.
ፖለቲካ	ፖለ.
ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ	ፖለ. ኢኮ.

የመዝገበ ቃላቱ አጠቃቀም

ይህን መዝገበ ቃላት በአግባቡ ለመጠቀም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የአጠቃቀም መመሪያዎች መከተል ይጠቅማል።

1. የሚፈለገው ቃል የት / እንዴት ይገኛል?

በዚህ መዝገበ ቃላት ውስጥ በፊደል ተራቸው ተደርድረው የሚገኙት ዋና ቃላት በሦስተኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር፣ ተባዕታይ ጾታ፣ የኃላፊ ጊዜ ቅርፅ የያዙ ግሶች ወይም ነባር ስሞች ወይም ደግሞ የት እንደሚገኙ ለመጠቆም ያህል የተመዘገቡ ውልድ ቃላት ናቸው። የመዝገበ ቃላቱ ተጠቃሚ የሚፈልገው ቃል ግስ ከሆነ ቃሉን በሦስተኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር፣ ተባዕታይ ጾታ፣ በኃላፊ ጊዜ ቅርፁ በፊደል ተራው ማግኘት ይችላል። ነባር ስሞችና የዋናው ግስ ውልድ ቃላትም እንደዚሁ በፊደል ተራቸው ይገኛሉ።

አልፎ አልፎ በመነሻነት የተመዘገቡት ቃላት በላያቸው ላይ የኮከብ / * / ምልክት ተደርጎባቸው እንመለከታለን። ይህ ምልክት የተደረገበት ቃል በተቀመጠበት ቅርፁ የማይነገር ወይም መነገሩ የቀረ ወይም አገልግሎቱ በተወሰነ አካባቢ ብቻ የሆነ ወይም ቀደም ሲል በመነሻነት ያገለግል ነበር ተብሎ የሚታሰብና ግምታዊ (መላምታዊ) በሆነ መንገድ የተሰጠ የግስነት ቅርፅ ነው። እነዚህ መላምታዊ ቅርፆች ግማሾቹ ባለ ሁለት እግር ግማሾቹ ደግሞ ባለ ሦስት፣ ባለ አራት ወይም ባለ አምስት እግር ሆነው ይገኛሉ። ይህ አይነቱ የቅርፅ መለዋወጥ የተፈጠረው ቃላቱ መላምታዊ በመሆናቸውና እንደ ሙሉ የሆነ የሰከነ ቅርፅ የሌላቸው ስለሆኑ ነው። የኮከብ ምልክት ተደርጎባቸው መግቢያቸው በአገልግሎት ላይ ተገኝተው እንደገቡ ሆነው እንዳይቆጠሩ ለማመልከት ነው።

በቋንቋው ውስጥ [illegible] የሚገለፁ ሆነው ነገር ግን በተናጠል ሊሰፍሩ የማይችሉ ቃላት [illegible] [illegible] እንዲሰፍሩ ወይም ረዳት ግስ እየተጣመረላቸው እንዲፈቱ ተደርጓል።

ምሳሌ፡

ማው^{1}

ማው (እማው) አለ ግ. ትልቅ ወይም ወፍራም ነገር ሲወድቅ፣ ሲሰበር ወይም ሲመታ የሚፈጥረውን አይነት ድምፅ አሰማ።

ማው^{2}

ማው አለ ግ. በሃይል ነደደ። እሳቱ ማው ብሎ ነደደ።

በመዝገበቃላቱ አሰራር የማንኛውም ውልድ ቃል ፍቺ የተሰጠው በሶስተኛ መደብ፥ ነጠላ ቁጥር፡ ተባእታይ ጾታ፡ ሃላፊ ጊዜ በተቀመጠው ግስ ስር በመሆኑ አንድን ውልድ ቃል በመዝገበ ቃላቱ ውስጥ ለመመልከት የሚፈልግ ተጠቃሚ የቃሉ መገኛ ወደሆነው የሶስተኛ መደብ፡ ነጠላ ቁጥር፥ ተባእታይ ጾታ፥ ሃላፊ ጊዜ ግስ ስር ሄዶ መፈለግ ይኖርበታል ማለት ነው። ለምሳሌ "**ስብራት**"፥ "**ሽልማት**"፡ "**መጥረጊያ**" የሚሉትን ቃላት የሚፈልግ ሰው እንደቅደም ተከተሉ "ሰበረ"፡ "**ሸለመ**"፥ "**ጠረገ** " በሚሉት ግሶች ስር መመልከት ይኖርበታል።

አለዚያም ቃላቱን በፊደል ተራቸው ሄዶ ቢመለከት ወደእነዚሁ ግሶች ሊመሩት የሚችልበት ሁኔታ አለ፡ ሆኖም ይህ ሁሌ የሚያጋጥም አይደለም። እንደ "**ተሰበረ**" ፥ "**ተፈለገ**"፡ "**አበላ**" የመሳሰሉ "ተደራጊ" ወይም "አድራጊ" ውልድ አእማዶች ወይም ከአእማዱ የተገኙ ውልድ ስሞችና ቅፅሎች መነሻ የሆኗቸውን ግሶች (ማለትም ከተሰጠው ምሳሌ አንፃር "ሰበረ"፡ "**ፈለገ**"፥ "**በላ**" የሚለውን) በቀላሉ መገመት ስለሚቻል በፊደል ተራቸው አልተቀመጡም። እነዚህን መሰል በ"**ተ** "፥ "ተሰ-"፥ "**ተሸ-**"፡ "**ተን-**"፥ "**አ-**"፡ "**አስ-**"፡ "**አሸ-**"፡ "**አን-**" የሚነሱ ቃላትን መገኛ ማወቅ ካስፈለገ በስተመጨረሻ አባሪ በሆነው የቃላት ዝርዝር ውስጥ መመልከት ይቻላል። መነሻቸውን መገመት የሚያስቸግሩ ውልድ የአእማድ ግሶች ወይም ቃላት ግን በአብዛኛው ወደሚገኙበት ተመላክተዋል።

ጥምር ቃል አብዛኛውን ጊዜ የመጀመሪያው አጣማሪ ቃል በሚገኝበት ቦታ የሚፈታ ስለሆነ የመጀመሪያው ከፊል ቃል ወደሚገኝበት ሄዶ መመልከት ያስፈልጋል። ለምሳሌ "**ቤተክርስትያን**" " **ቤት** " ስር የተሰራ ሲሆን " **ማብሪያና ማጥፊያ**" ደግሞ "በራ" በሚለው ስር ይገኛል።

2. አመዘጋገብ

በመነሻነት ወይም በውልድ ቃልነት የተመዘገቡት ቃላት ደመቅ ባለ ቀለም የተፃፉት ናቸው። በመነሻነት የተመዘገቡት ቃላት የዳርቻውን ጠርዝ ይዘው የተፃፉ ሲሆን ከነዚህ የሚገኙ ውልድ ቃላት ገባ ብለው ተመዝግበዋል። ከአንድ መነሻ ወይም ውልድ ቃል የሚገኙ ሃረጎች ወይም ዘይቤአዊ አነጋገሮች እንደውልዱ ቃል ደምቀውና ገባ ብለው ተመዝግበው ይገኛሉ።

አንድ ቃል በተባእታይ ጾታ ቅርፅ ቢመዘገብም ፍቺው ለሁለቱም ጾታ እንደሚያገለግል ሆኖ ተቀምጧል። ይሁንና አልፎ አልፎ አንድ ቃል በተለይም ግስ በአንስታይ ጾታ ሲነገር ተጨማሪ ሌላ ፍች የሚኖረው ከሆነ ቃሉ በአንስታይ ጾታ እንደማንኛውም መነሻ ወይም ውልድ ቃል ደመቅ ብሎ ከተፃፈ በኋላ ፍቺ ይሰጠዋል።

በአማራጭነት ወይም በተወዳዳሪነት የሚያገለግል የአንድ ቃል ሌላ መልክ ወይም ቅርፅ ወይም የአፃፃፍ መንገድ መደበኛውን ወይም በአብዛኛው የተለመደውን የአፃፃፍ ስርአት በማስቀደም በቅንፍ ውስጥ ተከትሎ ይመዘገባል:: የሚከተለውን ምሳሌ እንመልከት::

ሰበረ ግ ………………………	መነሻ ቃል
ሰበር ሰካ አለ ………………	ሃረግ
ሰብራት ስ ……………	ውልድ ቃል
ወለደ ግ ፩……………:: ፪………::	በተባእት ጾታ መነሻነት የገባ ቃል
ወለደች ……………………::	በአንስታይ ጾታ መነሻነት የገባ ውልድ ቃል
ረቡእ (ሮብ) ስ ………	አማራጭ ወይም ተወዳዳሪ ቃል

3. ልዩ ልዩ መረጃዎች

አንድ መነሻ ወይም ውልድ የሆነ ቃል ከተመዘገበ በሗላ ቃሉ ስም ሆኖ ብዙ ቁጥሩን ለየት ባለ መልክ የሚመሰርት ከሆነ የሚቀጥለው መረጃ ይህንኑ የሚመለከት ይሆናል፡ ይህም መረጃ ከቃሉ ቀጥሎ በቅንፍ ውስጥ ይሰጣል:: ለየት ባለ መልክ የሚመሰረቱ የብዙ ቁጥር ቅርፆች በቅንፍ ውስጥ እንዲቀመጡ ቢደረግም ከነዚህ ውስጥ አብዛኞቹ መደበኛውን የብዙት ስልት ሊከተሉ ይችላሉ:: ለምሳሌ፡-

ቄስ	→	ቀሳውስት	→	ቄሶች
ወፍ	→	አእዋፍ	→	ወፎች
መፅሃፍ	→	መፃህፍት	→	መፅሃፎች

ቃሉ መደበኛውን የአማርኛ ብዙ ቁጥር መመስረቻ ስርአት ብቻ ተከትሎ የሚሄድ ከሆነ ግን ከቃሉ ቀጥሎ የሚሰጠው መረጃ የንግግር ክፍል ነው:: ከንግግር ክፍሉ ቀጥሎ የምናገኘው ፍቺ ሲሆን ቃሉ ከአንድ በላይ ፍቺ ካለው ፍቺዎቹ እየተለዩ ይቀመጣሉ:: ቃሉ በተለያዩ የንግግር ክፍሎች የተለያዩ ፍቺዎች ካሉትም የፍቺው ተራ ቁጥር ከመጣፉ በፊት የንግግር ክፍሉ ይመዘገባል::

ለአንድ ቃል የተሰጠው ፍቺ በተወሰነ የስራ ወይም የእውቀት መስክ ብቻ የሚያገለግል ከሆነ ወይም የቃሉ አጠቃቀም ደረጃ ልዩ መግለጫ የሚያስፈልገው (ለምሳሌ ነውር፣ ተራ አነጋገር፣ ስድብ፣...) ከሆነ ይህው ሁኔታ ከፍቺው በፊት በቅንፍ ውስጥ ይቀመጣል::

አንድን ቃል ተከቶ ሊገባ የሚችል ቃል ከተተኪው ቃል ቀጥሎ በአንድ ህዝባር ምልክት ይለያል። ከህዝባር ምልክቱ ቀጥሎ ያለው ቃል ቀድሞት የገባውን አንድ ቃል ሊተካ ይችላል ማለት ነው። በተጨማሪም ህዝባር አንድን ቃል ለማብራራት የተሰጡ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ አስረጂዎችን ለመለያየት ወይም ለመከፋፈል ይገባል። የሚከተሉትን ምሳሌዎች እንመልከት።



ለሆተ ስ ስለት ለማውጣት የሚያገለግል ድንጋይ፤ መሳል።

መነሻ ቃል

የንግግር ክፍል

ፍቺ

የተለያዩ ፍቺዎችን መለያ ቁጥሮች

ለመለመ¹ ግ 1. ቅጠል አወጣ፤ አቆጠቆጠ፤ አጀፈጀፈ፤ ጨበጨበ።

2. አረንጓዴ ሆነ፤ ልምላሜ ተላበሰ። *አካባቢው ለምልሟል።*

ለምለም ቅ አረንጓዴ፤ ርጥብ፤ ሊጋ። *ለምለም ሳር።*

ውልድ ቃል

አስረጅ አረፍተ ነገር

በተመሳሳይ መንገድ የሚጠሩ(የሚነበቡ) ነገር ግን ዘራቸው የተለያየ ቃላትን መለያ ቁጥር

ለመለመ² ግ የዛፍን ወይም የአትክልትን ቅጠል ወይም ቅርንጫፍ በብዛት ቆረጠ፤ ቀጠፈ፤ መለመለ።

ለመዘገ (መዘለገ) ግ በሃይል፤ አጥብቆ ቀነበበ።

በአማራጭነት የሚያገለግል ቃል ወይም የአንድ ቃል ሌላ የመግቻ ቅርፅ

ለበን ስ ለንቦጭ፡ የታችኛ ከንፈር።

ለበኑን ጣለ አኮረፈ።

ዘይቤያዊ አገላለፅ ወይም ሃረግ

ለበናም ቅ (ስድብ) ለምቦጣም።

የቃሉ አጠቃቀም ደረጃ

ለት " **እለት** " ን ተመ.

ማጣቀሻ ወይም ማመላከቻ

ማብሁ "ግባ" ስር ተመ.

ማቢ ዝ.ከ.

ማብ ዝ.ከ.

ማንድስ "ገነደሰ" ስር "ገንዳሳ" ን ተመ.

ሊጦን ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) በቤተክርስቲያን ቄሶች በየእለቱ ተራ አስገብተው የሚያዜሙትና የሚደግሙት የምስጋና ፀሎት።

ቃሉ በዚህ ፍቺ የሚያገለግልበት የስራ ወይም የትምህርት መስክ

ላባ ኳስ ስ (ስፖ.) ክብ በሆነ ቡሽ ላይ የተሰካኩ ላባዎች ያሉት የባድሚንተን መጫወቻ።

ምላጭ ስ 1. ፀጉርን ለመላጨት የሚያገለግል ….። 2. ጠመንጃን፡ ሽጉጥን ለመተኮስ የምትሳብ….።
3. (ዘይ.) በአነጋገሩ ቀልጣፋ የሆነ፡ ብልጣብልጥ።

የዘይቤአዊ አጠቃቀም ፍቺን አመልካች

ሳብ አጠመቀው /አሰጠመው ከድንጋጤ፡ ከቀለም፡ ከሰማይ የተነሳ በባህር አሳበው።

ተኪ ቃልን ወይም ተመሳሳይ የሆኑ የአሰራር ሃረጎችን ወይም ቃሎችን ለማሳየት የሚያገለግል ምልክት

ታሪካዊ ቅ. በታሪክ የተመዘገበ ክንዋኔ የተካሄደበት፡ በታሪክ የሚታወቅ። *ታሪካዊ ስፍራዎች / ታሪካዊ ቅርሶች።*

ማጠቃለያ

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ይህ መዝገበ ቃላት በስራው ላይ በርካታ ሰዎች የተሳተፉበት መሆኑ የቃላት ተቀባይነትን ሚዛናዊ በማድረግና ልዩ ልዩ የስራና የልምድ ግብአቱን በማጎልበቱ ረገድ የጠቀመውን ያህል ፍች የተሰጠባቸውን ቋንቋና የፍች አሰፋፈር ስርአት ወጥነት በመጠበቅ ረገድ አሉታዊ ተፅእኖ አሳድሯል። አዲሱን የአማርኛ የፊደል ገበታ በመጠቀም ረገድም ይህ መዝገበ ቃላት የመጀመሪያ ሙከራ የተደረገበት ስለሆነ ለረጅም ዘመን በአገልግሎት ላይ የኖረው የቀድሞው የፊደል ገበታ እውቀት ተፅእኖ በስራው ልዩ ልዩ ደረጃዎች ጣልቃ እየገባ የመዝገበ ቃላቱን የፊደል አጠቃቀም ጥራት አውኳል። እንዲሁም የኮምፒዩተር ስራው የተሰራበት የአማርኛ ፊደል ፕሮግራም መደበኛነትና አንድ ወጥ ስርአት የሚጎድለው በመሆኑ በርካታ የፊደል ግድፈቶችን ፈጥሯል። ለምሳሌ 'ን' ተብሎ የተጻፈውን በብዙ ቦታዎች ወደ 'ነ' እየቀየረ ይሰራል። በእነዚህና በሌሎች መሰል ምክንያቶች መዝገበ ቃላቱ፡

—የፊደል ግድፈቶች፤

—የአፈታት ዘዴ ወጥነት ጉድለቶች፤

—የመነሻ ቃልና የውልድ ቃል አቀማመጥ ስርአት ስህተቶች፤

—የውልድ ቃላት የዘርፍ ወገኖች አመዳደብ ችግሮች፤

—የፍች ማመሳከሪያዎችና ማመላከቻዎች አለመቀናጀት፡ ወዘተ.

የመሳሰሉ እንከኖች ሊገኙበት እንደሚችል ግልፅ ነው። እነዚህን ግድፈቶች ለመንቀስና ለማረም በባለሙያዎች በኩል ከፍተኛ ጥረት የተደረገ ቢሆንም የተፈለገውን ያህል ጥራት ለማግኘት አልተቻለም። ሆኖም ጉድለቶቹ እጅግ የገነኑ መልእክትን ወይም አንባቢውን

የሚያፋልሱ እንዳይሆኑ ለማድረግና ተጠቃሚው እነዚህን ስህተቶች በቀላሉ ሊያርማቸውና ሊያቃናቸው ከሚችልበት ደረጃ ለማድረስ የተቻለውን ያህል ተሞክሯል።

የአማርኛ ቋንቋ እጅግ ውስብስብነት የበዛበትና የአንዳንድ ቃላት አፃፃፍና አጠራርም ገና መደበኛ መልክ ያልያዘ መሆኑ የመዝገበቃላቱን ጥራትና ወጥነት የመጠበቁን ጥረት እጅግ አድካሚ አድርጎታል። ለምሳሌ እንስሳ እንሰሳ፣ እፅዋት - እፀዋት፣ ማእርግ - ማእረግ፣ መፅሃፍ - መፀሃፍ፡ አትክልት - አታክልት፣ ረጅም - ረዥም፡ ... አይነት ልዩነቶችን እየተከታተሉ በአንድ ወጥነት የማስፈሩ ተግባር በጣም አስቸጋሪ ሆኗል።

በ "እፅ"ና በ"እፅዋት/እፀዋት" መካከል ያለው የነጠላና የብዙ ቁጥር ግንኙነትም የነጠላ ቁጥር ቅርፁ በተለየ ደረጃ አዲስ የሆነ ፅንሰሃሳብ መግለጫ ሆኖ በመለመዱ በፍች ወቅት ቃሉ በነጠላ ቁጥር ቅርፁ እንዳይሰፍር ተደርጓል። ከዚህ የተነሳ የፍቺው አረፍተነገር ሰዋሰዋዊ ህግ የቃሉን የነጠላ ቁጥር ቅርፅ የሚሻ መሆኑ እየታወቀ በግድ በብዙ ቁጥር ቅርፁ እንዲሰፍር ተደርጓል። በ "ፍሬ"ና በ "ፍራፍሬ"፣ በ "ነፍስ"ና በ "ነፍሳት"፣ ... መካከል ያለው የነጠላና የብዙ ቁጥር አጠቃቀም ይህንኑ የሚመስል ችግር ያለበት ነው። ስለሆነም የመዝገበቃላቱ ተጠቃሚዎች እነዚህንና ሌሎች መሰል ችግሮችን ከግምት ውስጥ ሊያስገቡ ያሻል።

ምንም እንኳ መዝገበቃላቱ በበርካታ ችግሮች መካከል በመዘጋጀቱ ከእንከኖች የፀዳ አለመሆኑ ግልፅ ቢሆንም ይህ የማንኛውም መዝገበቃላት ዝግጅት የሚያጋጥመው ችግር በመሆኑ ባለበት ደረጃ ለህትመት እንዲበቃ ተደርጓል። በዚህ መዝገበቃላት ውስጥ የሚታዩ ድክመቶችንና ጉድለቶችን በሁለተኛው እትም አርሞና ያብልጥ አስተካክሎ ለማቅረብ እቅድ ተይዟል። ከዚያ በመለስ ይህ እትም ረዘም ላለ ጊዜ የተደከመበትና ተፈላጊ የሆኑ ልዩ ልዩ መረጃዎች የሚገኙበት፣ በተለይም ለከፍተኛ ደረጃ ተማሪዎች፣ ለአስተማሪዎች፣ ለተርጓሚዎችና ለሌሎችም የጥናትና ምርምር ሰዎች በመረጃ ምንጭነት የሚያገለግል የማመሳከሪያ መፅሃፍ ነው። ከዚህም ባሻገር መዝገበቃላቱ ለአማርኛ ቋንቋ እድገትና መደበኛነት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ሊኖረው እንደሚችል ይታመናል።

ሀ

ሀ በአማርኛ የፊደል ገበታ መጀመሪያ ላይ የሚገኝ ፊደል (ግእዙ ሆሄ)::

ሁ የ "ሀ" ፊደል ካእብ ዘር::

-ሁ(-ኩ) በግስ መድረሻ በኩል እየተጨመረ "እኔ"የሚለውን የግሱን ባለቤት የሚወክል ምእላድ:: *ፃፍሁ (ፃፍኩ)*::

ሁለመና ስ ሁለንተና፣ ጠቅላላ አካል::

ሁለት ስ 1. በአንድና በሶስት መካከል ያለ ቁጥር መጠሪያ፣ በአሃዝ ሲፃፍ"፪"፥ "2" ነው:: ቅ 2. በአንድና በሶስት መካከል ያለ ብዛትን የሚያሳይ:: *ሁለት መጽሐፍት*:

ሁለት ሆነ ተገመሰ፡ ተከፈለ::

ሁለት ሆነች ወለደች፥ ተገላገለች::

ሁለት ልብ ሆነ አመነታ፥ ወላወለ፡ ሃሳቡ በአንድ አልፀና አለ::

ሁለት መልክ አወጣ ተጎሳቆለ፥ ከሳ፥ ጠቆረ::

ሁለት ፀጉር አወጣ/ አበቀለ ሸመገለ፥ በእድሜ ገፋ::

ሁለተኛ ቅ 1. ዳግመኛ:: 2.ሌላ፥ ተጨማሪ:: 3. በተራ ከመጀመሪያው ቀጥሎ የሚመጣ፥ የመጀመሪያው ተከታይ:: 4. በደረጃ ወይም በማእረግ ከአንደኛው ዝቅ ያለ:: 5. በደረጃ ወይም በማእረግ ከአንደኛው የሚበልጥ:: *የሁለተኛ ዓመት ዩኒቨርሲቲ ተማሪ*::

ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ስ ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት በኋላ የቀለም ወይም የቀለምና የሙያ ትምህርት የሚሰጥበት ትምህርት ቤት::

ሁለት ምላስ/አፍ ዋሾ፥ በፊት የተናገረውን ሽሮ ሌላ የሚናገር::

ሁለት ባህርይ ስ ኢየሱስ ክርስቶስ በአካላዊ ተዋህዶ የአምላክነትና የሰውነት ባህርያት አሉት የሚል ትምህርተ ሃይማኖት::

ሁለት ነጥብ ስ በእጅ ፅሁፍ ውስጥ ቃልን ከቃል ለመለየት በሁለት ቃላት መካከል ላይና ታች በመሆን የሚቀመጥ የስርአተ ነጥብ አይነት(፡)::

ሁለት አፍ ሰይፍ በሁለቱም ጎኑ ስለት ያለው ሰይፍ::

ሁለት እጅ እጥፍ::

ሁለት ፊት በሁለት በኩል፥ ሁለት ወገን::

ሁለንተና ስ ጠቅላላ አካል::

ሁለንተናዊ ቅ አጠቃላይ::

ሁሉ ቅ መላው፡ ጠቅላላው::

ሁሉ በሁሉ በጠቅላላው፥ በድምሩ:: *ሁሉ በሁሉ መቶ ብር ይሸጣል*::

ከሁሉ ከሁሉ በይበልጥ::

ሁለገብ (ሁልገብ) ቅ 1. በሁሉ ቦታ ሊገባ፡ ሊሰራ፡ ሊያገለግል የሚችል:: ስ 2. ቁመቱ በጣም አነስተኛ የሆነ፡ ለምችና ለሌሎችም በሽታዎች በመድሃኒትነት ያገለግላል የሚባል ቅጠለ ሸካራ የእፅዋት አይነት::

ሁሉም ቅ በሙሉ፡ በጠቅላላ::

ሁሉን አቀፍ (ሁልአቀፍ) ቅ በሙሉ፡ ሁሉን የሚያካትት፡የሚያጠቃልል::

ሁልቀን ተው.ግ በእየቀኑ፡ ዘወትር፣ ሁልጊዜ::

ሁልጊዜ (ሁሌ) ተው.ግ ዘወትር::

ሁልቆ መሳፍርት (እልቆ መሳፍርት)

ሁልቆ መሳፍርት የለውም ስፍር ቁጥር የለውም፥ እጅግ በጣም ብዙ ነው::

ሁር

ሁር ጠጣ 1. ነፃ ወጣ:: 2. ባዶውን ቀረ፡ ሙልጭ ወጣ::

ሁት (ውሃ) "ኩት (ውሃ)" ን ተመ.

ሁነኛ "ሆነ" ስር ተመ.

ሁናቴ "ሆነ" ስር "ሁኔታ"ን ተመ.

ሁኔታ "ሆነ" ስር "ሁኔታ" ን ተመ.

ሁከት "አወከ" ስር ተመ.

ሁዳዴ(ኩዳዴ) ስ ክርስቲያኖች ከፋሲካ በፊት የሚፆሙት የኢየሱስ ፆም፣ አቢይ ፆም::

ሁዳድ "ሆደደ^{1}" ስር ተመ.

ሂ የ "ሀ" ፊደል ሳልስ ዘር::

ሂስኛ "ሂስ" ስር ተመ.

ሂሳብ ስ 1. በአሃዞች አማካይነት እየተሰላ የሚቀመር የአራቱ መደቦች (መደመር ፥ መቀነስ፡ ማብዛት፥ ማካፈል) የስሌት ዘዴ፥በማልፅ በተወሰኑ ፅንሰ ሃሳቦችና ምልክቶች አማካይነት የብዛትን፥ የቅርፅን፥ የቅንብርንና የመጠንን ትክክለኛ ጠባይና ግንኙነት ለመግለፅ የሚያስችል የስሌት ሳይንስ:: 2. ለተገዛ ወይም ለተሸጠ ነገር ወይም ለአገልግሎት የሚከፈል ገንዘብ:: *ያለበትን ሂሳብ አልከፈለም*::

ሂሳቡን አስረከበ በልዩ ልዩ ምክንያት የተቀበለውን ወይም በእጁ የነበረውን ገንዘብ ለሚመለከተው ሰጠ::

ሂሳቡን አወራረደ የወጪና የቀረን ሂሳብ በማስረጃ ተሳሰበ::

ሂሳቡን አገኘ 1. ቅጣቱን አገኘ:: 2.

ድርሻውን አገኘ።

ሂሳብ አደረገ ወጪና ገቢን አመሳከረ፣ አሰላ፣ ተሳሰበ።

ሂሳብ አጣራ ገቢና ወጪውን አመሳክሮ ትክክለኛነቱን አረጋገጠ።

ሂሳብ ከፈተ ባንክ ቤት ውስጥ ገንዘብ ለማስቀመጥ የሚያስችለውን ፎርማሊቲ አሟልቶ ባንኩ ለደንበኞቹ ከሚሰጠው አገልግሎት ተጠቃሚ ሆነ።

ሂሳብ ዘጋ 1. በተወሰነ ጊዜ ለተወሰነ ስራ የተመደበን የገንዘብ ገቢና ወጪ በማመዛዘን ሂሳቡን አጠቃለለ። 2. የሚፈለግበትን እዳ ከፍሎ ጨረሰ። 3. በባንክ ውስጥ ያስቀመጠውን ገንዘብ በሙሉ ወሰደ።

በ ___ ሂሳብ በ ___ ዋጋ። *በ5 ብር ሂሳብ ገዛሁት።*

በምን ሂሳብ በምን ምክንያት።

በእገሌ ሂሳብ እገሌ በሚከፍለው፣ በእገሌ ገንዘብ።

ሂሳብ መርማሪ ስ በመንግስታዊ ወይም በህዝባዊ ድርጅት ውስጥ በተወሰነ ወቅት ገቢና ወጪ የሆነው ገንዘብ በህጉ መሰረት በትክክል በስራ ላይ መዋሉን መርምሮ አስፈላጊውን ሪፖርት ለሚመለከተው ክፍል እንዲያቀርብ ህጋዊ መብት የተሰጠው ግለሰብ ወይም ቡድን፣ ኦዲተር።

ሂሳብ ተቆጣጣሪ ስ በአንድ ድርጅት ውስጥ ተመድቦ የድርጅቱ የእለት ተእለት የገንዘብ ነክ እንቅስቃሴ በትክክል መካሄዱን የሚከታተልና የሚያረጋግጥ ሰራተኛ።

ሂሳብ ክፍል ስ የአንድ ድርጅት አጠቃላይ ሂሳብ ነክ እንቅስቃሴ የሚካሄድበትና ገንዘብ ነክ አገልግሎት የሚሰጥበት የአስተዳደር ዘርፍ።

[የ] ሂሳብ መኪና ስ አሃዛዊ ስሌቶችን (መደመር፣መቀነስ፣ማባዛት፣ማካፈል) በተቀላጠፈ ሁኔታና በትክክል ለማስላት የሚያስችል ዘመናዊ መሳሪያ።

[የ] ሂሳብ መዝገብ ስ የገንዘብ ወጪና ገቢ መጠን የሚሰፍርበት ደብተር፣ መዝገብ።

[የ] ሂሳብ መዝገብ አያያዝ ስ 1. የገቢና የወጪ ሂሳብ አመዘጋገብና አያያዝ ዘዴ። 2. የገቢና የወጪ ሂሳብ አመዘጋገብና አያያዝ ዘዴን የሚመለከት የትምህርት ዘርፍ።

[የ] ሂሳብ ሰራተኛ ስ ሂሳብ ነክ የሆኑ ጉዳዮችን የሚያከናውን ሰራተኛ።

[የ] ሂሳብ ሹም ስ የአንድን ድርጅት ገቢና ወጪ እንዲሁም ሌላ ሂሳብ ነክ እንቅስቃሴን በበላይነት የሚመራ ሃላፊ።

ሂስ ስ 1. በደካማ ጎን ላይ የሚያተኩር አስተያየትና ነቀፋ። 2. በአንድ የስራ ውጤት፣ በተለይም በስነ ጥበብ ስራዎች (በስነፅሁፍ፣ ቲያትር፣ ሙዚቃ፣ ስእል፣...) ላይ የሚሰነዘር መዘኛ አስተያየት ። 3. ድክመትን ወይም ስህተትን ለማረም ሲባል በተሳሳተው ወገን ላይ የሚቀርብ ቂም በቀል የሌለበት ትችት።

ሂሱን ዋጠ የተሰነዘረበትን ሂስ አምኖ ተቀበለ።

ሂሰኛ ቅ ተቺ፣ አቃቂር አውጪ።

ሃያሲ ስ አንድን የስራ ውጤት በተለይም ስነፅሁፍንና ሌሎችንም የስነጥበብ ስራዎች በተወሰኑ መመዘኛዎች እየለካና እየገመገመ አስተያየት የመስጠት ችሎታ ያለው ሰው።

ሂና ስ ሴቶች እጅና እግራቸውን እንደዚሁም ፀጉራቸውን የሚያቀሉበት የእንሶስላ አይነት።

ሂያጅ " **ሄደ**" ስር ተመ.

ሂደት ዝ.ከ.

ሂድ ዝ.ከ.

ሂጅ ዝ.ከ

ሃ የ "**ሀ**" ፊደል ራብእ ዘር።

ሃ ብሎ ጀመረ ከመነሻው፣ ከመጀመሪያው ጀመረ።

ሃ አለ 1. ፊደል ቆጠረ። *ሃ ሳይሉ ፅህፈት ሙሉ ሳይዙ ሙግት።* 2.ጀመረ። *ገና ሃ ከማለቱ ስራውን ጠላው።*

ከሃ እስከ ፐ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ። ***ጉዳዩን ከ ሃ እስከ ፐ አውቀዋለሁ።***

ሃሁ ስ 1. ፊደል ቆጠራ፣ የፊደል ትምህርት። 2. የመጀመሪያ ደረጃ እውቀት። ***የቴክኖሎጂ ሃሁ።***

ሃሁ አለ 1. ፊደል ቆጠረ፣ ተማረ። 2.መጠነኛ የሆነ ትምህርት አገኘ።

ሃላፊ "**አለፈ**" ስር ተመ.

ሃላፊነት ዝ.ከ.

ሃሎ (አሎ) በስልክ ጥሪ ጊዜ መልእክት ለመቀበል ወይም አድማጩ መስማቱን ለማረጋገጥ የሚባል ቃል።

ሃመል [እሳት] ስ በመጋቢት ወር የሚወጣ የኮከብ አይነት። በተጨማሪ '**ኮከብ ቆጠራ**'ን ተመ.

ሃመልማል ስ ልምላሜ፣ አረንጓዴነት።

ሃመር ቅ ቀይነት ያለው። *ሃመር ፈረስ።*

ሃምራዊ ቅ 1. ቀይነት ያለው። 2. ወይንማ።

ሃሙስ ስ በረቡእና በአርብ መካከል ያለው ቀን ስም፣ ከእሁድ ጀምሮ ሲቆጠር የሳምንቱ አምስተኛ ቀን።

ሃሚተኛ " **አማ** " ስር ተመ.

ሃሚና የ"ሳሊበሳ"ን 1ኛ ፍቺ ተመ.

ሃማል ስ ተሸካሚ፥ ኩሊ።

ሃሜታ "እማ" ስር "ሃሜት"ን ተመ.

ሃሜት "እማ" ስር ተመ.

ሃምሌ ስ ከሰኔ ቀጥሎ የሚመጣ የአመቱ 11ኛ ወር ስም።

ሃምራዊ "ሃመር" ስር ተመ.

ሃምሳ "አምሳ" ን ተመ.

ሃምስ ስ እንደ " ሄ "፥ "ሌ " ፥ "ሜ" ፥ ... ያሉ በራብእና በሳድስ መካከል የሚገኙ የአምስተኛዎቹ ፊደላት ዘሮች መጠሪያ ወይም የድምፅ ምልክቶች።

ሃምበርገር ስ የተፈጨ ወይም በስሉ የተቆረጠ ስጋ ከተጠበሰ በኋላ ለሁለት በተሰነጠቀ ዳቦ ውስጥ ተጨምሮ የሚዘጋጅ ምግብ።

ሃሞት (አሞት) ስ ከጉበት ውስጥ የሚመነጭና በሆድ እቃ ውስጥ ምግብን ለማላም የሚረዳ ቅጠልማ ቀለም ያለው መራራ ፈሳሽ።

ሃሞቱ ፈሰሰ ተስፋ ቆረጠ፥ ደከመ፥ ዛለ።

ሃሞተ መራራ ቅ ኀበዝ፥ ቆራጥ፥ ወኔ ያለው፥ ክስታራ።

ሃሞተ ቢስ ቅ ወኔ ቢስ፥ መንፈስ ደካማ፥ ፈሪ።

ሃረግ ስ 1. ከአጠገቡ በሚገኙ ዛፎችና ቋሚ ነገሮች ላይ እየተጠመጠመ ወይንም መሬት ለመሬት እየተሳበ የሚያድግ እንደ ሓቦ፥ ጠዘ፥ ሃረግ ራሳ ያለ የእፅዋት አይነት። 2. ለጌጥ ሲባል በጥርብ እንጨት፥ በመፃህፍት፥ በሃውልቶችና በልዩ ልዩ ነገሮች ላይ እንደ ሃረግ እየተጠላለፈ የሚሰራ ንድፍ። 3. ሁለትና ከሁለት በላይ የሆኑ ቃላት የሚገኙበት፥ ማሰሪያ አንቀፅ የሌለው የአረፍተ ነገር ክፍል። ምሳ. የሆነው ሆኖ /ወደ ቤቱ፥ ...።

ሃረጉን ቆጠረ /መዘዘ የዘር ሃረጉን ዘረዘረ፥ ትውልዱን ቆጠረ።

ሃረግ ጣለ የሃረግ ንድፍ ሰራ።

ሃረግ ራሳ (አረግ ራሳ) ስ ሰዎች ለምች መድሃኒትነት የሚጠቀሙበት የሃረግ ወገን የሆነ የእፅዋት አይነት።

ሃሩር ስ 1. ከፍተኛ የፀሃይ ሙቀት፥ ቃጠሎ። 2. ቆም ፀሃፊዎች ጭማቂውን ለጥቁር ቀለም መበጥበጫ የሚጠቀሙበት እስኪያር ድረስ ተቆልቶ የተቀቀለ የስንዴ ወይም የገብስ ውሃ።

ሃራ ዘመን ስ አንድ ሰው በየአመቱ ስለሚያጋጥመው መጥፎም ሆነ ጥሩ ነገር በቅድሚያ ለማወቅ የሚደረግ በከዋክብ ቆጠራ ላይ የተመሰረተ ትንበያ።

ሃራም ስ ክልክል፥ ግዝት፥ እርም የሆነ ነገር (ብዙውን ጊዜ በእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች አካባቢ የሚነገር)።

ሃራራ ስ የቡና፥ የጫት፥ የትንባሆ ሱስ፥ ፍላጎት።

ሃራጅ ስ እንዲሸጥ የተወሰነ ንብረት በጨረታ ወይም ገበያ ላይ በተገኘው ዋጋ የሚሸጥበት መንገድ።

በሃራጅ ሸጠ በአንድ ጨረታ ወይም ገበያ ላይ በተገኘው ዋጋ ሸጠ።

ሃር ስ 1. ለስላሳ የሆነ፥ እንደሸረሪት ድር ያለና ከሃር ትል የሚገኝ ነጭ ፈትል። 2. ከሃር ወይም ሃርን ከመሰለ ፈትል የሚሰራ፥ እንደአስፈላጊነቱ በልዩ ልዩ ቀለማት የሚዘጋጅ ለስላሳ ጨርቅ፥ ልብስ።

የሃር ትል ስ የሃር ድር የምትሰራ ትል።

ሃርሞኒካ ስ በትንፋሽ ወይንም በንፋስ የሚሰራ ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያ(ስእሉን የሙዚቃ መሳሪያ ስር ተመ.)።

ሃር አምባ

ሃርአምባና ቆቦ የተራራቀ፥ የማይገናኝ፥ የማይመሳሰል (ሁኔታ፥ ነገር፥ ቦታ)።

ሃሰት ስ 1. ውሸት፥ አብለት፥ ቅጥፈት። ቅ 2. ትክክለኛ ወይም እውነተኛ ያልሆነ። *የሃሰት ምስክር።*

ሃሰተኛ ቅ 1. ውሸታም። 2. ትክክለኛና እውነተኛ ያልሆነ። *ሃሰተኛ የገንዘብ ኖት።*

ሃሳብ (አሳብ) ስ 1. በአእምሮ ውስጥ የሚቀረፅ፥ የሚታቀድ፥ የሚመላለስ ፅንሰ ነገር፥ ግንዛቤ። 2. ስጋት፥ ጭንቀት። *ሃሳብ የሆነብኝ የልጄ ነገር ነው።* 3. አላማ፥ እቅድ፥ ፍላጎት። 4. አስተያየት። *በዚህ ጉዳይ ላይ ሃሳብህ ምንድን ነው?*

ሃሳቡ ተቃለለ ጭንቀቱ፥ ችግሩ ተወገደ።

ሃሳቡ ተከፈለ 1. አመነታ፥ ሁለት ልብ ሆነ። 2. ሃሳቡ ተቃለለ።

ሃሳቡን ለወጠ ውሳኔውን ሻረ።

ሃሳቡን ቆረጠ ወሰነ፥ አንድ ልብ ሆነ።

ሃሳቡን አነሳ 1. ያቀረበውን ሃሳብ ተወ። 2. ሃሳብ አመነጨ፥ አቀረበ።

ሃሳቡን ጣለ ደንታ ቢስ ሆነ፥ ስለችግሩ ማሰብ ተወ፥ አረፈ፥ ተደላደለ።

ሃሳቡን ፈፀመ አላማውን ከግቡ አደረሰ፥ አሳካ።

ሃሳብ ተቀበለ አስተያየት፥ ምክር ጠየቀ፥ ሰማ ወይም ተቀበለ።

ሃሳብ አቀረበ አስተያየት ሰጠ።

ሃሳብ አካፈለ አስተያየት ወይም ምክር ሰጠ

ሃሳብየለውም/የለበትም 1. ችግር

የለበትም። 2. ለምንም ነገር ኣይጨነቅም፣ደንታ ቢስ ነው።

ሃሳብ የለሽ ቅ የሚያሳስበው፣ የሚያስጨንቀው ነገር የሌለበት።

ሃሳብ ያዘው /ገባው የሚያሳስብ ነገር አጋጠመው፥ ጨነቀው።

በሃሳብ ተዋጠ ስለአንድ ነገር በማሰላሰል አእምሮው ተያዘ፥ ተከዘ።

በሃሳብ ተግባቡ በኣላማ፣ በፍላጎት ተስማሙ።

ሃሳበ ቢስ ቅ ግድ የለሽ፥ ደንታ የሌለው።

ሃሳበ ብኩን ቅ የረጋ ሃሳብ የሌለው።

ሃሳበ ውሱን ቅ ጠባብ ኣመለካከት ያለው፥ ኣርቆ የማያስተውል።

ሃሳበ ግትር ቅ እኔ ያልኩት ካልሆነ የሚል፣ ስህተት መሆኑን ቢያውቅም ኣንድ ጊዜ የያዘውን ኣስተያየት ለመለወጥ የማይሻ፣ መንቻካ።

ሃሳባዊ (ብ.ቁ. **ሃሳባውያን**) ስ 1.የሃሳባዊነት ፍልስፍና ተከታይ። ቅ 2. በሃሳባዊ ፍልስፍና ላይ የተመሰረተ (ኣመለካከት)።

ሃሳባዊነት ስ ሃሳብን ከቁስ ኣካል የሚያስቀድም የፍልስፍና ኣመለካከት ወይም ሃሳብ የቁስ ኣካል መገኛ ነው የሚል የፍልስፍና ዘርፍ።

ሃሳዊ ቅ ዋሾ፥ ቀጣፊ፥ ሃሰተኛ።

ሃሳዊ መሲህ ስ 1. ያልሆነውን ነኝ የሚል ኣታላይ፥ ኣሳሳች ጠቢይ። ቅ 2. ኣሳሳች፥ ሃሰተኛ (ሰው)።

ሃሴት ስ ደስታ።

ሃሴት ኣደረገ ተደሰተ፥ ፈንጠዝያ ኣደረገ።

ሃሺሽ ስ ሱስ የሚያሲዝና ኣእምሮን የሚያስት ኣደንዛዥ እፅ።

ሃቅ¹ ስ 1. እውነት፥ ትክክል የሆነ፣ የተረጋገጠ ነገር ። 2. የራስ ድርሻ፥ እንጀራ ንብረት።

ሃቀኛ ቅ እውነተኛ፥ ትክክለኛ።

ሃቅ² (**ኣቅ**) ስ ሰስት ክንድ ርዝመት ያለው የብትን ልብስ ወይም የሸማ መጠን፥ ልክ።

ሃበሻ (**ኣበሻ**) ስ የኢትዮጵያ ህዝብ የሚጠራበት ኣጠቃላይ ስም።

[የ] ሃበሻ ልብስ ስ ከጥጥ ፈትል በሸማኔ የሚዘጋጅ የኢትዮጵያውያን ልብስ።

[የ] ሃበሻ ቀሚስ ስ ነጠላና ቀሚስ ሆኖ የተዘጋጀ የሃበሻ ልብስ።

[የ] ሃበሻ ጎመን ስ በኣንድ ላይ እጅብ ብሎ የሚበቅልና ቁመቱ ኣጠር ብሎ ቅጠሉ ኣነስ ኣነስ ያለ የጎመን አይነት።

ሃብሃብ ስ ቅርፁ ሞላላ ወይም ክብ የሆነ፣ ዱባ የሚመስል፥ ውስጡ ቀይ ሆኖ ጥቋቁር ፍሬዎች ያሉትና ጣፋጭ ውሃ በብዛት የያዘ የፍራፍሬ አይነት፤ ተክሉም ሃብሃብ ይባላል፤

ሃብል ስ አንገት ላይ ለጌጥ የሚደረግ ከብር ወይም ከወርቅና ከመሳሰሉት ማእድናት የሚሰራ ቀጭን ሰንሰለት።

ሃብት ስ 1.ንብረት፥ ጥሪት። 2. እድል፥ እጣ።

ሃብቷ ቀና እድሏ ኣማረላት፥ ተሳካላት፥ ኣገባች (ልጃገረድ)።

ሃብቱ ቀና ቅ እድለኛ።

ሃብተ ሰባራ/ ሰንኩል ቅ እድለ ቢስ።

ሃብተ ሲጋ ስ ምድራዊ ፀጋ፥ ሃብት።

ሃብተ ቢስ ቅ እድለ ቢስ።

ሃብትሽ በሃብቴ ስ ባልና ሚስት ከተጋቡ በሂላ የሚያፈሩት ንብረት የሁለቱም የጋራ እንዲሆን የሚያደርግ የጋብቻ ውል፥ ስምምነት።

ሃብታም ቅ 1. ባለፀጋ፣ ባለብዙ ንብረት፥ ከበርቴ። 2.(ዘይ.) እድለኛ።

ሃቤየስ ኮርፐስ ያለፍርድ ቤት ትእዛዝ ላልተወሰነ ጊዜ መታሰርን የመቃወም መብት ወይም ኣንድን ሰው በእስር ለማቆየትም ሆነ ላለማቆየት ብይን ይሰጥበት ዘንድ ፍርድ ቤት እንዲቀርብ የሚያደርግ የፅሁፍ ትእዛዝ።

ሃተታ "**ኣተተ**" ስር ተመ.

ሃች ኣምና (**ታች ኣምና፥ ካች ኣምና**) ስ ከኣምና በፊት የነበረው ኣመት።

ሃኔ ስ ለማረጃና ለማወራረጃ የሚያገለግል እንደ ደጋን የጎበጠ ሰፊ ጎራዴ።

ሃኔ

ሃኪም ስ የህሙማንን በሽታ ኣይቶና መርምሮ ኣስፈላጊውን እርዳታ የሚሰጥና መድሃኒት የሚያዝ፥የሚያክም የጤና ባለሙያ።

ሃኪም ቤት ስ የጤና ምርመራና የህክምና ተግባር የሚከናወንበት ተቋም።

የሃኪም እረፍት ስ ሃኪም የሚሰጠው ወይም የሚያዘው እረፍት።

የሃኪም ወረቀት ስ ሃኪም መድሃኒት ያዘዘበት ወይም ስለህመሙ የተናገረበትና ኣስተያየት የሰጠበት ፅሁፍ።

ሃካይ ቅ ከፉ፥ ተንኮለኛ።

ሃኬት ስ ተንኮል፥ ክፋት።

ሃኬተኛ ቅ ተንኮለኛ፥ ክፉ።

ሃዋላ ስ በባንክ ወይም በፖስታ ቤት አማካይነት ገንዘብ የሚላክበት መንገድ፥ ሰዲ።

ሃዋርያ (ብ.ቁ. **ሃዋርያት**) ስ 1. ወንጌልን ለማስተማር በክርስቶስ ተመርጦ የነበረ አስተማሪ ወይም መምህር (ተመርጠው የነበሩት 12 ሃዋርያት ናቸው)። 2. የአንድ የተወሰነ አይነት እምነት ወይም ትምህርት ግንባር ቀደም ሰባኪ፥ አስተማሪ።

ሃውልት ስ በሰው ወይም በሌላ አምሳል ከድንጋይ ወይም ከነሃስ፥... የተሰራ መታሰቢያ

ሃውልትየሆን ስራ ሰራ ቋሚና ጠቃሚ የሆነ ስራ ሰራ።

ሃውዛ "**አውዛ**"ን ተመ.

ሃዘን (አዘን) ስ 1.ለቅሶ፥ ቁይታ። 2. ትካዜ፥ መከፋት።



ሃውልት

ሃዘኑን ገለፀ ያዘነ መሆኑን አሳወቀ።

ሃዘን ላይ ነው 1. ለቅሶ ላይ ነው። 2. ትካዜ ላይ ነው፥ ተከፍቷል።

ሃዘን ገባው በጣም አዘነ፥ ተከዘ፥ ተከፋ።

[የ] ሃዘን ተካፋይ ለቅሶ ወይም ሃዘን ባለበት ቦታ በመገኘት አለዚያም የተሰማውን ሃዘን በተለያየ መንገድ (በደብዳቤ፥ በስልክ፥...)በመግለፅ የሟችን ቤተሰብ የሚያሰናና ወዳጅ፥ ዘመድ።

ሃዘኔታ "**አዘን**" ስር "**እዘኔታ**" ን ተመ.

ሃዘንተኛ ቅ ዘመድ ወይም ወዳጅ የሞተበትና በለቅሶ ላይ ያለ።

[የ] ሃዘን ልብስ ስ በሃዘን ጊዜ የሚለበስ ጥቁር ልብስ፥ ከል።

[የ] ሃዘን ቤት ስ ለቅሶ ቤት።

ሃያ ስ 1. በአስራ ዘጠኝና በሃያ አንድ መካከል ያለ ቁጥር መጠሪያ፥ በአሃዝ ሲፃፍ "፳" ፥ "20" ነው። ቅ 2. ብዛቱ ሁለት አስሮችን የሚያህል። *ሃያ ሰዎች።*

ሃያል (ብ.ቁ. **ሃያላን**) ቅ 1. ብርቱ፥ ጠንካራ፥ ጉልበታም፥ ሃይለኛ። 2. ሁሉን ማድረግ የሚችል። *ሃያሉ እግዚአብሄር።*

ሃያላን መንግስታት ስ በባህል፥ በፖለቲካና በኢኮኖሚ የበለፀጉና በሌሎች አገሮች ላይ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ተፅእኖ ለማድረግ የሚችሉ አገሮች (ሩሲያ፥ ቻይና፥ አሜሪካ፥ እንግሊዝና ፈረንሳይ)።

ሃያሲ "ሂስ" ስር ተመ.

ሃይ^1

ሃይ አለ ግ ከለከለ፥ አገደ፥ ተቆጣጠረ፥ ገሳገሰ።

ሃይ^2

ሃይ በል (ሃይ በሌ) አለ ግ አጣደፈ፥ አፋጠነ (ስራን፥ መንገድን፥ ...)።

ሃይል ስ 1. ብርታት፥ ጥንካሬ፥ ጉልበት፥ አቅም። 2. አንድን ተግባር የሚፈፅም ቡድን። 3. ዘዴን ያልተከተለ አስገዳጅ ግፊት።

በሃይል ተው.ግ. 1. በብዛት፥ ከመጠን በላይ፥ በጣም። *በሃይል መጠጣት ሰውነትን ይጎዳል።* 2. በጠና፥ እጅግ በጣም። *በሃይል ታሟል።* 3. ጉልበትን በመጠቀም፥ በማስገደድ።

ሃይለ ቃል ስ 1. የሃይል፥ የቁጣ ንግግር። 2. በአንድ ፅሁፍ ወይም ንግግር ውስጥ ዋናውን ሃሳብ ወይም ፍሬ ነገር የያዘ ቃል፥ ሃረግ፥ አረፍተ ነገር።

የሃይል ሚዛን ስ ከሌላው ወገን ጋር ሲነፃፀር በመብለጥ ወይም በማነስ የሚታይ የሃይል፥ የጉልበት፥ የአቅም መጠን።

የሃይል ስራ ስ በዘዴ፥ በብልሃት ያልሆነ፥ የጉልበት ስራ።

ሃይለኛ ቅ 1. ኀበዝ፥ ብርቱ፥ ጉልበተኛ፥ ጠንካራ። 2. ከባድ። *ሃይለኛ ዝናም።* 3. ቁጡ፥ የማይበገር፥ ግልፍተኛ ኮስታራ።

ሃይማኖት ስ አለምን የፈጠረና ተፈጥሮን በበላይነት የሚቆጣጠር መለኮታዊ ሃይል እንዳለ የሚቀበል በእምነት ላይ የተመሰረተ አመለካከት፥ እምነት።

ሃይማኖቱን ለወጠ የነበረውን (ይዞት የቆየውን) ሃይማኖት ትቶ የሌላ ሃይማኖት ተከታይ ወይም አማኝ ሆነ።

ሃይማኖት ያውርድ አውደማ ተጥሎ ወይም ማእድ ቀርቦ ሳለ የሚደርስ እንግዳ ምርቱ ይበርክት፥ ማእዱ ይባረክ ለማለት የሚናገረው የመልካም ምኞት መግለጫ ቃል።

ሃይማኖተኛ ቅ 1. የተቀበለውን ወይም የሚከተለውን ሃይማኖት ትእዛዝና ስርአት በፅኑ የሚያከብር አማኝ። 2. ጠንካራ፥ ቃሉን የማያጥፍ ታማኝ።

ሃይማኖተ ቢስ ቅ በቃሉ የማይፀና፥ ከሃዲ።

ሃይማኖተ አበው ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ቀደምት የሆኑ የክርስትና ሃይማኖት ሊቃውንት ያዘጋጁት ሃይማኖታዊ ትምህርትን የያዘ መፅሃፍ።

ሃይማኖታዊ ቅ ሃይማኖት ነክ የሆነ፥ በእምነት ላይ የተመሰረተ።

ሃይቅ ስ ዙሪያውን በመሬት የተከበበ ስፋትና ጥልቀት ያለው የውሃ ክምችት።

ሃይድሮጅን ስ ከንጥረ ነገሮች ሁሉ ቀላል

የሆነና ከኦክስጂን ጋር ሲዋሃድ ውሃን የሚያስገኝ፣ ቀለምና ሽታ የሌለው በቀላሉ የሚነድ ጋዝ።

ሃይድሮጅን ቦንብ ስ ከፍተኛ የሃይድሮጅን ክምችት የያዘና እጅግ በጣም ታላቅ ጥፋት ሊያደርስ የሚችል ቦንብ።

ሃይጅን ስ የጤና አጠባበቅ ትምህርት።

ሃዲስ ኪዳን "**አደሰ**" ስር "**አዲስ ኪዳን**"ን ተመ.

ሃዲድ ስ ለባቡር መሄጃ በመሬት ላይ የተዘረጋ የተጋደመ መሰላል የሚመስል የብረት ንጣፍ።

ሃዲድ ብረት ስ ጠንካራ የሆነ የብረት አይነት።

ሃጅ^1 ስ ወደ መካ መዲና የሚደረግ የእስልምና ሃይማኖታዊ ጉዞ።

ሃጂ ስ መካ መዲና ደርሰው የተመለሱ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች የሚጠሩበት የአክብሮት ስም።

ሃጅ^2 "**ሄደ**" ስር "**ሂያጅ**"ን ተመ.

ሃገር (አገር) ስ 1. በውስጡ ህዝቦች የሚኖሩበት፣ የተወሰነ ጂኦግራፊያዊ ክልል ያለውና በአንድ መንግስታዊ አስተዳደር ስር የሚገኝ ግዛት። 2. በተወሰነ ጂኦግራፊያዊ ክልል ውስጥ ያለ መሬት። 3. የትውልድ ስፍራ ወይም አካባቢ። 4. (ዘይ.) በተወሰነ ክልል ውስጥ የሚኖር ህዝብ። *ሰውየውን አገር ይወደዋል።*

ሃገሩን ሸጠ ለግል ጥቅሙ ሲል የሃገሩን ጥቅም ለሌላ ወገን አሳልፎ ሰጠ።

አገር ነው 1. ብዙ ነው። *የገዛሁት ቡና አገር ነው።* 2. ሰፊ ነው። *አዳራሹ አገር ነው።*

አገር አጠፋ ህገወጥ ስራ ሰራ፣ ጥፋት አደረሰ።

አገር አጥፊ ቅ ስርአት የለሽ፣ ባለጌ።

አገር ፈታ አወከ፣ አስቸገረ።

አገሬው ህዝቡ።

ሃገረሰብ ቅ 1. ባህላዊ ወይም የባህል። *የሃገረሰብ መድሃኒት።* ስ 2. ገጠር፣ አገር ቤት። 3. ያገር ቤት ሰው።

አገረ ገዢ ስ በንጉስ ይሾም የነበረ አገር አስተዳዳሪ።

አገር ምድሩ 1. ስፍራው፣ አካባቢው ሁሉ። 2. ሁሉም፣ ጠቅላላው።

አገር ቂጥ ቅ በጣም ሩቅ።

አገር በቀል ቅ ሃገር ውስጥ የተገኘ፣ የተቋቋመ።

አገር ቤት ስ ከከተማ ውጭ የሆነ አካባቢ፣ ገጠር፣ ባላገር።

አገር አቋራጭ ቅ ረጅም ርቀት ያለው፣ ረጅም ርቀት የሚጓዝ። *አገር አቋራጭ ውድድር /አገር አቋራጭ አውቶቡስ ።*

አገር ወዳድ ቅ ሃገሩንና ወገኑን የሚወድ፣ ብሄራዊ ስሜት ያለው።

አገር ወገብ ስ በቆላና በደጋ መካከል የሚገኝ ቦታ፣ ወይና ደጋ።

አገር ጎብኚ ስ የተለያዩ ቦታዎችን፣ ታሪካዊ ስፍራዎችን፣...እየተዘዋወረ የሚጎበኝ ሰው፣ ቱሪስት።

[የ] ሃገር ልብስ ስ 1. በአንድ ሃገር ወይም በተወሰነ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች የሚለብሱት ባህላዊ ልብስ። 2. ሃበሻ ልብስ።

የሃገር ልጅ/ሰው ስ የአንድ ሃገር ወይም የአንድ አካባቢ ተወላጅ።

የሃገር ሽማግሌ ስ ህዝብ የሚያከብረው፣ ወግንና ስርአትን የሚያውቅ አዛውንት።

የሃገር ቀንድ ስ ታዋቂ፣ ዋንኛ ሰው።

የሃገር ባህል ስ ባህላዊ የሆነ፣ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣና የተለመደ ወግ፣ ስርአት፣...።

የአገር አባት ስ የተጣላ የሚያስታርቅ ሽማግሌ፣ አዛውንት።

ሃገርኛ ቅ የሃገር ውስጥ የሆነ።

ሃጋይ ስ ከታህሳስ 26 እስከ መጋቢት 25 ያለውና ከመፀው ቀጥሎ የሚመጣ፣ ሙቀትና ድርቅ የሚታይበት የበጋ ወቅት፣ አጋይ።

ሃግ

ሃግ አለ ግ ገሰፀ፣ ተቆጣ፣ መከረ።

ሃጢአት ስ 1. ሃይማኖት የማይፈቅደው ስራ ወይም ድርጊት 2. ክፉ ስራ፣ ጥፋት፣ ወንጀል። 3. በፍትወተ ስጋ ግንኙነት ጊዜ ከወንድ ብልት የሚወጣ ፈሳሽ ዘር።

ሃጢአት ገባ /ሰራ ሃይማኖቱ የማይፈቅድለትን መጥፎ ስራ ሰራ ወይም አደረገ።

ሃጢአተኛ ቅ 1. ሃይማኖቱ የማይፈቅድለትን ስራ የሰራ። 2. ወንጀለኛ፣ በደለኛ፣ ክፉ ሰሪ።

ሃጥእ (ብ.ቁ. **ሃጥአን**) ስ ሃጢአተኛ ሰው።

ሃጫ ቅ ነጭ፣ በረዶ የሚመስል።

ሃጫ በረዶ ስ ደቃቅ በረዶ።

ሃፍረት "**አፈረ**" ስር "**እፍረት**"ን ተመ.

ሄ የ"ሀ" ፊደል ሃምስ ዘር።

ሄሄ "**አሄሄ**"ን ተመ.

ሄሊኮፕተር ስ በላይዋ ላይ ባሉት ጠፍጠፍ ያሉ ተሽከርካሪ ዘንጎች አማካኝነት ለመብረርና በትንሽ ቦታ ላይ ለማረፍ የምትችል የአውሮፕላን አይነት።

ሄደ ግ 1. ተጓዘ፣ ገሰገሰ፣ ተራመደ። 2. ስፍራን

ለቀቀ። *ከዚህ አካባቢ ሄደለ።* 3. (ዘይ.) ግብረስጋ ፈፀመ። *ከሴት መሄድ ጀምሯል።* 4. በዘ፣ ኖረ፣ ባለማቋረጥ ቀጠለ። *የህዝብ ቆጠራ ሄደ።* 5. ተሸጠ። *ሊታው በስንት ብር ሄደ?* 6. ተስማማ። *ሸሚዙ ከኮቱ ጋር ይሄዳል።*

ሂያጅ (ሃጅ) ቅ 1. መንገደኛ፣ ተጓዥ። 2. ገስጋሽ። 3. የማይቆይ፣ የማይሰነብት። 4. (ዘይ.) ሴሰኛ።

ሂደት ስ ወደ ውጤት የሚያመራ፣ የተከታተለና የተያያዘ ድርጊት፣ ክንዋኔ፣ እንቅስቃሴ።

ሂጃ ስ አሂዶ

መሄጃ ስ 1. መራመጃ፣ መተላለፊያ መንገድ። 2. መጠጊያ ዘመድ፣ ረዳት። 3. መሸሻ። 4. መሳፈሪያ ገንዘብ። 5. መጓጓዣ (መኪና፣ በቅሎ፣...)።

ተካሄደ ግ ተከናወነ፣ ተሰራ።

አሄደ ግ 1. የእህልን ክምር በአውድማ ላይ ዘርግፎ በከብቶች እግር አበራዩ፣ እህሉን ወቃ። 2. የትርጓሜ መምህር ምስጢረ መፃህፍትን በአንድምታ ትርጓሜ እየተነተነ አስተማረ፣ አስረዳ። 3. የትርጓሜ ተማሪ ምስጢረ መፃህፍትን በአንድምታ ትርጓሜ ተማረ፣ አወቀ። 4. በሃይል መታ፣ ደበደበ።

አሂዶ ስ በከብቶች አማካይነት በአውድማ ላይ እህል የመውቃት ወይም የማበራየት ስራ፣ ሂጃ።

አህያጅ ስ ለእህል ውቂያ በአውድማ ላይ የሚዞሩ ከብቶችን ከኋላ ከኋላቸው እየሄደ የሚነዳ ሰው።

አካሄደ ግ 1. አንቀሳቀሰ፣ መራ፣ ሰራ (ሰራን)። 2. አጠናቀቀ፣ አከናወነ፣ ፈፀመ። 3. በአውድማ ላይ የአሂዶን ስራ አገዘ ወይም ረዳ።

ማካሄጃ ስ ማንቀሳቀሻ፣ ማከናወኛ። *ለስራው ማካሄጃ ገንዘብ ተገኝቷል።*

አካሄድ ስ 1. አረማመድ። 2. ሁኔታ፣ አኳኋን፣ አዝማሚያ፣ አቅጣጫ። *የነገሩ አካሄድ አላማረኝም።*

አስሄደ ግ አቀላጠፈ፣ ቶሎ ቶሎ ሰራ።

ያስኬዳል 1. ያስችላል፣ ያዋጣል። *ለሱ ያለውም ዘዴ ያስኬዳል።* 2. ይወስዳል፣ ያደርሳል። *ይህ መንገድ ወደ ባሕር ዳር ያስኬዳል።* 3. ለመሄድ ወይም ለመራመድ ወይም ለማለፍ ያስችላል፣ ያመቻል። *ይህ መንገድ በመኪና ያስኬዳል?* 4. ይወስዳል፣ ይፈጃል። *ከአዲስ አበባ ናዝሬት በመኪና ሁለት ሰዓት ያህል ያስኬዳል።*

ህ ተ "ህ" ፊደል ሳድስ ዘር።

-ህ^{1} 1. በግስ መጨረሻ እየገባ የሁለተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር ፣ ተባእታይ ፆታ ባለቤትን የሚያመለክት ምእላድ (ለምሳሌ "መቼ መጣህ" በሚለው ግስ ውስጥ "-ህ" "አንተ" የሚለውን ባለቤት አመልካች ምእላድ ነው)።

-ህ^{2} በግስ መጨረሻ እየገባ የሁለተኛ መደብ፣ ነጠላ ቁጥር፣ የተባእታይ ፆታን ተሳቢነት የሚያመለክት ምእላድ (ለምሳሌ " አስተማረህ" በሚለው ግስ ውስጥ " -ህ" "አንተን" የሚለውን ተሳቢ አመልካች ምእላድ ነው)።

-ህ^{3} 1. በስም ላይ እየተጨመረ የሁለተኛ መደብ ባለቤትነትን ወይም ባለ ገንዘብነትን የሚያመለክት ምእላድ። (ለምሳሌ " መፅሃፍህ " በሚለው ቃል ውስጥ " ህ " " ያንተ " የሚለውን የባለገንዘብነት ሁኔታ የሚያመለክት ምእላድ ነው።) 2. አድራጊን ወይም ድርጊት ተቀባዩን የሚያመለክት ምእላድ። *መሄድህ በጀ/ መታሰርህ ተሰምቷል።*

ህለተ ወርቅ ስ በትረ መንግስት፣ የወርቅ ዘንግ።

ህሊና ስ ክፉና ደግን ለመለየት የሚያስችል አእምሮ ወይም ልቦና።

ህሊናውን ሳተ አእምሮውን አጣ፣ ሳተ።

ህሊና ቢስ ቅ የማያመዛዝን፣ የማያገናዝብ፣ ይሉኝታ የሌለው።

የህሊና ወቀሳ ስ በሰሩት ጥፋት ወይም ስህተት የሚመጣ ፀፀት።

የህሊና ፀሎት ስ ድምፅ ሳያሰሙ የሚደረግ ፀሎት።

የህሊና ፍርድ ስ በራስ አእምሮ ሁኔታን በማመዛዘን የሚሰጥ ፍርድ።

ህልም ስ 1. በእንቅልፍ ልብ ወይም በእንቅልፍ ላይ እንዳሉ የሚታይ ሃሳብ፣ ድርጊት ወይም ራእይ። 2. (ዘይ.) የማይሳካ፣ ከንቱ ምኞት።

ህልም ህልም (እልም እልም) አለ በጣም ጥቂት ወይም ትንሽ ተሰማ። (ለማጣፈጫ የሚጨመር ጨው፣ ስኳር፣....)።

ህልም ሆኖ ቀረ ሳይፈፀም፣ ሳይሳካ፣ ተግባራዊ ሳይሆን ቀረ።

ህልም ያርገው/ይሁን የተባለው ክፉ ወይም መጥፎ ነገር ውሸት ይሁን፣ አይፈፀም፣ አይድረስ ለማለት የሚነገር የምኞት መግለጫ አባባል።

ህልመ ሌሊት ስ በእንቅልፍ ልብ በተመስሎ የሚፈፀም የፍትወተ ስጋ ግንኙነት።

የህልም ሩጫ የማይሳካ፣ ከንቱ፣ ዋጋ ቢስ ልፋት።

የህልም እንጀራ የማይገኝ፣ ባዶ፣ በተስፋ ብቻ ያለ፣ ከንቱ ምኞት።

ህልመኛ ቅ ሊያገኝ ከሚችለው በላይ የሚመኝ።

ህልውና ስ ኑሮ፣ የመኖር ባህሪ።

ህልውና አገኘ 1. ተመሰረተ፡ ተቋቋመ። 2. መኖሩ ታወቀ፡ ህጋዊ ሰውነት አገኘ።

ህልውናው ተጠበቀ የመኖር መብቱ ተጠበቀ።

የህልውና ጥያቄ የመኖር ወይም ያለመኖር ጥያቄ። *ስራ ማግኘትና አለማግኘት የህልውና ጥያቄ ነው።*

ህልፈት "አለፈ" ስር **"እልፈት"**ን ተመ.

ህመም ስ 1. በሽታ፡ ደዌ፡ ጤና ማጣት። 2. ከበሽታ የተነሳ የሚሰማ ስሜት፥ ስቃይ።

ህመምተኛ ቅ በሽተኛ፡ ጤንነቱ የተጓደለ።

ህሙማን (ነጠ.ቁ **ህሙም**) ስ. ህመምተኞች።

ህማማት (ማማት) ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ ፡ ከሆሳእና ማግስት ጀምሮ እስከ ቅዳሜ ስኡር ያለው ጊዜ።

ህማማተ መስቀል ስ በወንጌል እንደተፃፈው ኢየሱስ ክርስቶስ በዕለተ አርብ የተቀበላቸው 14ቱ ስቃያት (መያዝ፡ መታሰር፡ በጥፊ መመታት፥ መገረፍ፡...)።

ህም ህም አለ ግ 1. ህም ህም የሚል ድምፅ አሰማ። 2. አጉተመተመ።

ህቅ

ህቅታ ስ ስርቅታ።

ህቅ አለ ግ ሞተ፡ አረፈ።

ህቡእ ቅ ድብቅ፥ ስውር፥ ምስጢራዊ።

ህቡእ ድርጅት ስ አባሎቹ እነማን እንደሆኑ እንዳይታወቅ በማድረግ ተግባሩን በምስጢር የሚያከናውን የፖለቲካ ድርጅት ወይም ሌላ ማህበር።

ህብር ቅ 1. በጠባይ ወይም በግብር ተመሳሳይነት ያለው። 2. ላዩን ሲያዩት ባለ አንድ ትርጉም ብቻ የሚመስልና ሲመሰጠር ግን ከአንድ በላይ የሆነ ትርጉም ያለው ቃል፥ ሃረግ።

ህብረ ቀለም ስ የልዩ ልዩ ቀለማት ቅንብር፥ ቅንጅት።

ህብረ ትርኢት ስ እንደዘፈን፥ ውዝዋዜ፥ ድራማ፥ አስቂኝ ቀልዶች፥... የመሳሰሉ ልዩ ልዩ መዝናኛዎች የሚቀርብበት የቴሌቪዥን ዝግጅት።

ህብር ቅኔ ስ በአንድ ቃል ወይም ሃረግ አማካይነት ሰምና ወርቁ ተቀናብሮ የሚገኝበት የቅኔ አይነት።

ህብረት ስ የተለያዩ ሰዎች ወይም ወገኖች ሃይላቸውን፡ እውቀታቸውን፥ ተግባራቸውን አስተባብረው ወይም አቀናጅተው በአንድነት የሚሰሩበት የመረዳዳት ሁኔታ፤ ስምምነት።

በህብረት ተውግ በጋራ፥ በአንድነት፥ በመደጋገፍ፥...።

ህብረተሰብ ስ 1. በተወሰነ አካባቢ አንድ አይነት ስርአትን፥ ህግን፡... እየተከተለ የሚኖር ህዝብ። 2. የስራቸው ወይም የኑሯቸው ቦታና ሁኔታ የሚያገናኛቸው ሰዎች ባጠቃላይ። *የዩኒቨርሲቲ ህብረተሰብ።*

ህብረተሰባዊነት ስ በላብአደሩ የበላይ ገዥነት የሚመሰረት፡ የማምረቻ መሳሪያዎች በህዝብ ቁጥጥር ስር የሚሆኑበት ስርአተ ማህበር ወይም የዚህን ስርአተ ማህበር አይቀሬነትና ትክክለኛነት የሚያስተምር ርእዮተ አለም።

[የ] ህብረት ሱቅ ስ በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች ለኑሮ የሚያስፈልጋቸውን ሸቀጣሸቀጥና የፍጆታ እቃዎች በቀላሉ ለማግኘትና በተመጣጣኝ ዋጋ መግዛት እንዲችሉ በማሰብ በጋራ የሚያቋቁሙት ሱቅ፥ መደብር።

[የ] ህብረት ስምምነት ስ በአንድ ድርጅት አሰሪና በድርጅቱ ሰራተኞች መካከል የሚደረግ ውል፥ ስምምነት።

[የ] ህብረት ስራ ማህበር ስ ሰዎች የኢኮኖሚ፥ የፖለቲካና የማህበራዊ ኑሮ ፍላጎታቸውን ለማሟላት እንዲረዳቸው በሙያቸው አንፃር ወይም ለአንድ አይነት ተግባር የሚመሰርቱት ማህበር፡ ድርጅት። (ለምሳሌ የገበሬዎች አምራቾች ህብረት ስራ ማህበር፥ የእደጥበባት ባለሙያዎች አምራቾች የህብረት ስራ ማህበር፡ የመኖሪያ ቤት የህብረት ስራ ማህበር፡...)።

ህብስት ስ 1. ለዝክር፡ ለማህበር፥... የሚጋገር ዳቦ፡ ፀዲቅ። 2. እንደ ድፎ ወፈር ሳይል የተጋገረ ክብ ዳቦ።

ህብስተ መና ስ መልኩ ያማረ፡ ጣእሙ የሚጣፍጥና ነጭ የሆነ ክብ ዳቦ።

ህትመት "አተመ" ስር ተመ.

ህንፃ ስ ለመኖሪያም ሆነ ለሌላ ስራ አገልግሎት እንዲሆን ከድንጋይ፡ ከሸክላ፡ ከብረትና ከመሳሰሉት ነገሮች የሚሰራ ፎቅ ያለው ወይም የሌለው ቤት።

ህንፃ ተቋራጭ ስ የኮንትራት ውል ተዋውሎ እንደ ህንፃና ድልድይ የመሳሰሉትን የግንባታ ስራዎች የሚሰራ ግለሰብ ወይም ድርጅት።

ህክምና ስ ህሙማንን ለማዳን (ለማከም) በሃኪሞች የሚደረግ እርዳታ፥ ክትትል።

ህዋ ስ ከምድር ከባቢ አየር ክልል ውጪ የሆነ ባዶ ቦታ።

ህዋስ (ብ.ቁ.**ህዋሳት**) ስ 1. ረቂቅ የሆነ አንድ አይነት ተግባር የሚያከናውንና ህይወት ያለው የማንኛውም አካል መሰረተ ነገር። 2. ለአንድ አይነት አላማ በተቋቋመ ማህበር ወይም የፖለቲካ ድርጅት ውስጥ የሚገኝ፡ የተወሰኑ አባላትን የሚይዝና እንቅስቃሴዎችን የሚያደርግ የድርጅት

አነስተኛ ክፍል።

ሀውከት "አወከ" ስር **"ሁከት"**ን ተመ.

ህዝባር ስ ፊደላትን፣ ቃላትን፣ ቁጥሮችን ፣...ለያይቶ፥ ከፋፍሎ፥ ከልሎ ለማስቀመጥ የሚያገለግል ወደቀኝ ዘንበል ያለ ቀጥተኛ መስመር(/)።

ህዝብ ስ 1. በተወሰነ መልክአምድራዊ ክልል ውስጥ የሚገኙና በአንድ መንግስት ስር የሚተዳደሩ ጠቅላላ ሰዎች። 2.የአንድ ብሄር ወይም ብሄረሰብ፣ጎሳ፣... አባል የሆኑ ሰዎች። 3. በአንድ አካባቢ በብዛት የሚታዩ፣ የሚገኙ ወይም የሚኖሩ ሰዎች ባጠቃላይ። 4. በመንግስት ስልጣን ውስጥ የሌሉ ተራ ሰዎች።

ህዝብ አዳም ስ (ተራ እነ.) ሰው ሁሉ።

ህዝበ ክርስቲያን ስ የክርስትና እምነት ተከታዮች፥ ምእመናን።

[የ] ህዝብ ቆጠራ ስ የአንድን ሃገር ህዝብ ብዛት ለማወቅ የሚደረግ የሰዎች ምዝገባ።

ህዝባዊ ቅ የህዝብ ወይም የህዝብ ወገን።

ህዝባዊ መንግስት ስ ለህዝብ ጥቅም የቆሙ፥ መሪዎቹ በህዝብ እየተመረጡ ህዝብን የሚያገለግሉበት መንግስት።

ህዝባዊ ሰራዊት ስ የመደበኛ ሰራዊት አባል ያልሆኑ፥ ከህዝብ ተውጣጥቶ የጦር ትምህርት የተከታተለና አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ወታደራዊ አገልግሎት የሚሰጥ ሃይል።

ህዝባዊ አመፅ ስ የተጨቆነ ህዝብ በጨቋኝ ገዢ መደብ ላይ የሚያካሂደው የአልገዛም ባይነት ትግል።

ህዝባዊ ድርጅት ስ በሙያ፣ በስራ፥ በፆታ፣ በእድሜ፥ በአካባቢ ወይም በሌላ ተመሳሳይ ማህበራዊ ግንኙነት ባላቸው ሰዎች የሚመሰረት ማህበር።

ህያው ቅ 1. በህይወት ያለ። 2. ዘላለማዊ።

ህይወት ስ 1. ለመራባት፥ ለማደግ፣ ለመንቀሳቀስ የሚያስችል ሃይል፤ ነፍስ። 2. የሰው ኑሮ። *በአደጋው ብዙ ህይወት ጠፋ።* 3.እድሜ፣ የኑሮ ዘመን። *በህይወቴ እንደዚህ ያለ ነገር አላየሁም።* 4- የአኗኗር ሁኔታ። *ህይወቱን በገዛ እጁ አበላሸ።*

ህይወቱን ሰጠ ራሱን መስዋእት አደረገ።

ለ___ ህይወቱን ሰጠ ለ_____ ጊዜውን፣ ጉልበቱን ወዘተ. አዋለ።

ህይወቱን አጠፋ ራሱን ገደለ።

የህይወት ታሪክ ስ አንድ ሰው በህይወቱ ዘመን ውስጥ ያሳለፈበት የኑሮ ሁኔታ፣ የፈፀመው ድርጊትና ያጋጠመው ነገር ዝርዝር።

የህይወት ዋስትና ስ የህይወት መድን፣ የሞት አደጋ በሚደርስበት ጊዜ በውሉ መሰረት ክፍያ እንዲደረግ የሚያስችል፣ ከመድን ድርጅት ጋር ግለሰብ ወይም ድርጅት የሚያደርገው ስምምነት።

ህዳር ስ ከጥቅምት ቀጥሎ የሚመጣ የአመቱ ሶስተኛ ወር።

ህዳር ታጠነ እንደወረርሽኝ ያሉ በሽታዎችን ለማጥፋት ሲባል በየአመቱ ህዳር 12 ቀን በየቀዬው ጭስ ተጨሰ።

ህዳግ ስ በአንድ ፅሁፍ ራስጌና ግርጌ እንዲሁም ጎንና ጎን ላይ የሚገኝ የማይፃፍበት ባዶ ቦታ።

ህግ (ብ.ቁ.ህግጋት) ስ 1.የመንግስት ጥበቃ የሚደረግለትና ሲጣስ ቅጣትን የሚያስከትል የማህበራዊ ግንኙነት መመሪያ፣ ደንብ። 2. አንድ ድርጊት የሚካሄድበት ስርአት፣ደንብ። *የእግር ኳስ ጨዋታ ህግ።* 3. ክብረንፅህና፣ ድንግልና።

ህግ አደረሰ ክብረንፅህናዋን ገሰሰ (በሚስትነት ያገባትን ልጃገረድ)።

ህግ ወጣ ደንብ ወይም ስርአት ወጣ፣ ታወጀ፣ ተደነገገ።

ህግ አወጣ ደንብ ወይም ስርአት አወጣ፣ ደነገገ፣ አወጀ።

ህግ አውጪ ስ ያንድን ሃገር ህግ ለማውጣት ስልጣን የተሰጠው የመንግስት አካል።

ህግ ይጠብቅህ /ያግድህ ስነስርአት ይኑርህ፣ ለህግ ተገዛ።

ህግ ገባ 1 ቃል ኪዳን አሰረ፣ አጨ። 2 በህግ አገባ።

ህግ ጣሰ ደንብ ወይም ስርአት ተላለፈ።

ህግ ፊት ቆመ በሰራው ጥፋት ተከሰሰ፣ ለፍርድ ቀረበ።

ህጓን ወሰደ ክብረ ንፅህናዋን ገሰሰ።

በህግ አምላክ አድራጎትህ ትክክል አይደለምና ህግ ያግድህ፥ የምታደርገውን አቁም ለማለት የሚነገር ቃል።

በህግ አገባ በህጋዊ መንገድ ልጃገረድ አገባ።

ህገ መንግስት ስ አንድ ሃገር የምትተዳደርበትና ህዝቦቿ ለሚያከናውኗቸው ተግባሮች ሁሉ መርህ የሚሆናቸው የሁሉም የበላይ የሆነ ህግ።

ህገ ወጥ ቅ 1. በህግ ያልተፈቀደ። 2. ስነስርአት የሌለው፥ ህግ አፍራሽ፣ ወንበዴ።

ህግ መምሪያ [ምክር ቤት] የህግ ረቂቅ የሚወጣበት የፓርላማ ክፍል።

ህግ መወሰኛ [ምክር ቤት] ስ የህግ ረቂቅን የማፅደቅ ወይም የመሻር ወይም የመወሰን፣.... መብት ያለው የፓርላማ አካል።

ህግ ማመንጨት ለሚመለከተው ባለስልጣን ቀርበው እንዲመክርባቸውና በህግ መልክ

እንዲወጡ በማለት መብት በተሰጠው አካል የህግ ሃሳብ ማፍለቅ።

የህግ ሚስት ስ 1. ውል በመፈራረም ወይም ባህሉ በሚፈቅደው ስርአትና ደንብ መሰረት የተገባች ሴት፣ የሰማኒያ ሚስት።2. በልጃገረድነቷ የተገባች የመጀመሪያ ሚስት።

የህግ ረቂቅ (ረቂቅ ህግ) ስ ህግ ሆኖ እንዲወጣ ለህግ አውጪው ክፍል የሚቀርብ የህግ ንድፍ።

የህግ ባል ስ 1. ውል በመፈራረም ወይም ባህሉ በሚፈቅደው ስርአትና ደንብ መሰረት የተገባ ባል። 2. የመጀመሪያ ባል።

[የ] ህግ አማካሪ ስ አንድን ድርጅት ወይም ግለሰብ በሚመለከት ለሚነሳ ክርክር ወይም ጉዳይ የህግ አስተያየት የሚሰጥ፥ የሚያማክር የህግ ባለሙያ።

የህግ ጠበቃ "**ጠበቀ**^{2}" ስር "**ጠበቃ**"ን ተመ.

ህጋዊ ቅ በህግ የተፈቀደ።

ህጋዊ ሰውነት ስ ለአንድ ድርጅት ፥ማህበር፥... በመንግስት የሚሰጥ የህልውና ፈቃድ ወይም እውቅና።

ህጥር ስ ሽቶ። *በህጥር በስንቡል መች አጠኑኝ ይላል፥ አመር ያለው ገላ እንዲያው ደርሶ ያምራል።*

ህፀፅ ስ እንከን፣ ጉድለት።

ህፃን (ብ.ቁ.**ህፃናት**) ስ 1. እድሜው እስከ አምስት አመት አካባቢ የሚደርስ ልጅ፣ ጨቅላ። 2. (ዘይ.) ከእድሜው ጋር ሲነፃፀር አስተሳሰቡ ያልበሰለ፥ ጨቅላ የሆነ።

ህፈረት "**አፈረ**" ስር "**እፍረት**"ን ተመ.

ሆ^1 **የ "ሀ"** ፊደል ሳብእ ዘር።

ሆ^2 (በቡሄ በሉ ጭፈራ ላይ በሆታ ተቀባዮች የሚባል። ለምሳሌ ቡሄ በሉ ሆ! ልጆች ሁሉ ሆ!...።

ሆታ ስ በህብረት የሚካሄድ የጭፈራ ዘፈን።

ሆሆታ ስ ሁካታ፣ ግርግር፣ የብዙ ሰዎች ድምፅ።

ሆ አለ ግ 1. ዘፈነ፥ ጨፈረ። 2. ንብን ለማስፈር ሆ የሚል ድምፅ አሰማ።

ሆ ብሎ ተነሳ በወኔና በአንድነት ተነሳ።

ሆሄ (ብ.ቁ **ሆሄያት**) ስ ከግእዝ እስከ ሳብዕ (ለምሳሌ ከ ሀ-ሆ ወይም ከ ሀ-ፐ) ያለው የፊደላት ስምና መልክ ወይም ቅርፅ።

ሆሆ (ሆሆይ) ቃ.አ. የአንክሮ፥ የማድነቅ፥ የማጋነን ቃል ወይም አነጋገር። *ሆሆይ! እውነት ሰው ጨረቃ ላይ ወጣ?*

ሆመር "**ሮቃ**"ን ተመ.

ሆመጠጠ "**ኮመጠጠ**"ን ተመ.

ሆማ " **አሆማ**"ን ተመ.

ሆምጣጣ "**ኮመጠጠ**" ስር "**ኮምጣጣ**"ን ተመ.

ሆረጠ (ኮረጠ) ግ ኮሰተረ፣ ክሽን ብሎ ጣፈጠ (ቀይ ወጥ)።

ሆሳእና ስ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ኢየሩሳሌም በአህያ ተቀምጦ ሲገባ ሰዎች ዘንባባ ይዘው የተቀበሉበትን እለት በማስታወስ የሚከበር፣ ከፋሲካ በፊት በሚገኘው እሁድ የሚውል በአል።

ሆቴል ስ የመኝታ ወይም የመኝታና የምግብ አገልግሎት የሚሰጥ፥ ብዙ ክፍሎች ያሉትና ብዙ ሰዎችን ሊያስተናግድ የሚችል የኪራይ ቤት።

ሆስቴስ ስ በአውሮፕላን ውስጥ የምታገለግል የሴት አስተናጋጅ።

ሆስፒታል ስ በይዘቱ ከክሊኒክና ከጤና ጣቢያ የሚሰፋ፣ በተመላላሽነት ወይም በሆስፒታሉ ተኝተው የሚታከሙ ህሙማንን እየተቀበለ አስፈላጊውን የጤና አገልግሎት የሚሰጥ የህክምና ተቋም።

ሆቴል ስ የመኝታና የምግብ አገልግሎት የሚሰጥ የንግድ ድርጅት።

ሆነ ግ 1. ተፈፀመ፣ ተደረገ፣ ተከናወነ። *ያልኩት ሆነ ።* 2. በጀ፣ ረባ፥ ጠቀመ፥ ፈየደ። *ሲጃራ የምታጨሰው ምን ይሆነኝ ብለህ ነው?* 3. ቀና፣ ተሳካ፣ ተሟላ። 4. ተስማማ። *ለገሩ ሆኖታል።* 5. *ልክ መጣ፣ በቃ። ልብሱ ሆኖኛል።* 6. አንድን አይነት፣ መጠን፣ መልክ፣ ባህርይ፣ ግብር፥ ስራ ያዘ። *ቀይ ሆነ/ትልቅ ሆነ / ደግ ሆነ /አስተማሪ ሆነ፥...።* 7. ተቀመጠ፣ ኖረ። *ከአባቱ ዘንድ ሆኖ ትምህርቱን ይማራል።* 8. በእኩል ተገኘ። ጉዳዩን በመካከላችን ሆኖ ገለፀልን።

ም ሆነ- 1.ወይም። *እሱም ሆነ እሷ መልእክቱን ሊያደርሱ ይችላሉ።* 2. እና፣ ሁሉም። *እሱም ሆነ እሷ መማር አለባቸው።*

ሆነ ብሎ (ሆነኝ ብሎ፣ ሆን ብሎ፣ ይሆነኝ ብሎ) አውቆ፣ አስቀድሞ አስቦበት። *ሆን ብሎ ነው ይህን ያደረገው።*

ሆኖም መፃ. ግን፣ ነገር ግን።

ለመሆኑ እንዲያው ለነገሩ፥ የሆነውስ ሆነና።

ለማይሆን ነገር /ጉዳይ ለማይረባ ወይም ለማይጠቅም ነገር (ጉዳይ) *ለማይሆን ነገር ገንዘብህን አታባክን።*

ሲሆን [ሲሆን] 1. ቢቻል። *ሲሆን አንተ ራስህ እንድትመጣ።* 2. እንደእውነቱ ከሆነ። *ሲሆን ወላጆችህን መርዳት ነበረብህ።*

ስለሆነ [ም] መፃ. ስለዚህ፥ በዚህ ምክንያት።

በሆነ ባልሆነ[ው] በሚረባ በማይረባው፣ በትልቁ በትንሹ። *በሆነ ባልሆነው አትጨቃጨቁ።*

በመሆኑ [ም] መዋ. በዚህ ምክንያት፡ በዚህ የተነሳ።

ቢሆን 1. ቢያሻ፥ ቢያስፈልግ። *ለቅሶ የሚደረስ ቢሆን እንነግራችሁ ነበር።* 2. ሲባል። *ፋንታ ቢሆን ይሰጡህ ነበር።*

ቢሆንም (ቢሆንም ቅሉ፡ ቢሆንም እንኳ) ያም ቢባል፡ ያም ቢደረግ። *ኋለበተሆም ሲሉኝ ነበር፤ ቢሆንም መጠየቁ አይቀርም።*

ቢሆንም ባይሆንም ለሁሉም፥ ለማንኛውም፡ ቢሳካም ባይሳካም።

ባይሆን ሌላው ቢቀር። *ዝም ብለህ ሳትቀር፤ ባይሆን ስልክ ደውል።*

አይሆንም እምቢ አይቻልም፡ አይደረግም።

እንደሆን ይሁን ባወጣ ያውጣው፡ እንዳሻው ይሁን።

እንዳልሆነ ሆነ እንዳልነበረ ሆነ፡ ተበላሸ፡ ተጎሳቆለ።

ከመሆኑም በላይ ከዚህም ሌላ፤ በተጨማሪ።

የሆኖ ሆኖ 1. ለማንኛውም። *ስራውን ተከታተልልኝ፤ የሆኖ ሆኖ እኔም እመጣለሁ።* 2. ነገር ግን። *መድሃኒት እየወሰደ ነው፤ የሆኖ ሆኖ አልተሻለውም።*

የሆነ ነገር እንዲገለጥ ያልተፈለገ ወይም ያልታወቀ አንዳች ነገር። *ስለ እሱ የሆነ ነገር ሰምቻለሁ/ በእጁ የሆነ ነገር ይዟል።*

የሆነውን 1. የተገኘውን። *ከቁም ሳጥን ውስጥ የሆነውን ልብስ ሰጠኝ።* 2. የነካውን፡ የአጋጠመውን። *የሆነውን ሳላውቅም ተከዟል።*

የሆነው ይሁን 1. የፈለገው ይሁን፡ የመጣው ይምጣ። *የሆነው ይሁን መሄዴ አይቀርም።* 2. የተገኘውን። *የሆነው ይሁን ብቻ ግዛልኝ።*

የሚሆን የሚደርሱ፡ የሚያህሉ። *ሃያ የሚሆኑ....።*

የማይሆን ነገር የማይታመን፡ የማይመስል ነገር።

ያም ሆነ ይህ ለማንኛውም፥ በማንኛውም መንገድ።

ይሁን እሺ።

ይሁንና መዋ. ነገር ግን፡ ሆኖም።

ይሁን እንጂ መዋ. ይሁንና፡ ነገር ግን።

ይሆናል ሳይሆን አይቀርም። *ገንዘቡን የወሰደው እሱ ይሆናል።*

ሁነኛ ቅ 1. ቁም ነገረኛ፡ ታማኝ። 2. አይነተኛ፡ ተስማሚ፡ ጠቃሚ።

ሁኔታ (ሁናቴ) ስ 1. አኳኋን፡ አዝማሚያ። *የጊዜው ሁኔታ አላማረኝም።* 2. ሁለንተና፥ ነገረ ስራ። *ሁኔታዋ እናቷን ትመስላለች።* 3. ነገር፡ ጉዳይ፡ ድርጊት። *ጠቅላላ ሁኔታውን ገለፀልኝ።* 4. ምክንያት። *በምን ሁኔታ ነው ትምህርቱን ያቋረጠው።* 5. ይዞታ። *መጀመሪያ የቤቱን ሁኔታ ለየውና ስለ ኪራዩ እንነጋገራለን።*

ተኋኋነ ግ ተስማማ፡ ተግባባ። *እኔና እሱ አልተኋኋንም።*

አኋኋነ ግ አስማማ፥ አግባባ።

አኳኋን ስ አዝማሚያ፡ አስተያየት፡ አመለካከት፡ አደራረግ።

ሆናና ቅ ሞኝ፡ ቂል።

ሆያ ሆዬ ስ በቡሄ፥ በዘመን መለወጫና በመስቀል በአል ጊዜ ወንዶች ልጆች የሚዘፍኑት የጭፈራ ዘፈን።

ሆይ[1] አክብሮትን፡ ፍቅርን፡.... ለመግለፅ ከስም ጋር እየተጣመረ የሚነገር ቃል። *አባታችን ሆይ/ ወንድሜ ሆይ፥ ...።*

ሆይ[2]

ሆይ ሆይ አለ ግ 1. አበረታታ፡ በል በል አለ፡ ገፋፋ። 2. አዋከበ፡ አቻኮለ። 3. አሸቃበጠ፡ አጣደፈ። *ከመጣው ሁሉ ጋር ሆይ ሆይ ማለት ይወዳል።*

ሆደደ[1] ግ በሰፌው አረሰ።

ሁዳድ (ኩዳድ) ስ ገባሮች እየተገደዱ የሚያርሱት የንጉስ፥ የመልከኛ፡... ይዞታ የነበረ ሰፊ የእርሻ መሬት።

የሁዳድ ፊራ ስ ሁዳድን ሳያርስ በቀረ ገበሬ ላይ የሚጣል ቅጣት።

ሁዳደኛ ስ ሁዳድ አራሽ።

ሆዳጅ ስ ገባር፡ ጭሰኛ።

ተሆደደ ግ ታረሰ፡ ተዘራ፡ ታረመ፥ ታጨደ፥ ተወቃ (የሁዳድ እርሻ)።

ሆደደ[2] ግ ሁዳዴን ፆመ።

ሁዳዴ በፊደል ተራው ተመ.

ሆድ ስ እንደ ጨጓራ፡ ጉበት፡ ኩላሊት፡ አንጀት፥..... የመሳሰሉት የሚገኙበት የሰውነት ክፍል(ስእሉን ሰውነት ስር ተመ.)።

ሆደ መርዝ ቅ ክፉ፡ ቂመኛ።

ሆዱ መረዘ ቂም ያዘ፡ ጥላቻ አደረበት።

ሆዱ ራስ /ቅቤ ጠጣ የልቡ ደረሰ፡ የፈለገው ነገር ስለሆነለት ተደሰተ።

ሆዱ/ልቡ ሻከረ ተቀየመ፤ ቅር ተሰኘ።

ሆዱ/አንጀቱ ቆረጠ አርግፍ አድርጎ፥ ጨክኖ ተወ።

ሆዱ/አንጀቱ ቡጭ ቡጭ አለ የማዘን፡ የመራራት ስሜት ተሰማው።

ሆዱ አረረ/ቆሰለ/ተቃጠለ ተናደደ።

ሆዱ/ልቡ/ አንጀቱ ነፈረ በጣም ተናደደ፣ ተበሳጨ።

ሆዱ አይታወቅም/አይገኝም አመሉ፣ ጠባዩ፣ ሃሳቡ አይታወቅም።

ሆዱ/ልቡ አይጠራም ቂም ይይዛል፣ ልቡ ንፁህ አይደለም።

ሆዱ ጎሸ ተቀየመ።

ሆዱ ጎደለ ተራበ።

ሆዱ/ ልቡ ጠራ ከተንኮል ወይም ከቂም በቀል ራቀ፣ ልበ ንፁህ ሆነ።

ሆዱ ጠቡቷል ከመወፈር የተነሳ ምግብ አይደፍርም፣ አይበላም።

ሆዱን/ ልቡን ሰጠ ያለውን ሃሳብ፣ ምስጢር ገለፀ፣ አካፈለ።

ሆዱን/ልቡን ቆረቆረው ከነከነው፣ ቅር አለው።

ሆዱን ቆረጠው ቆረቆረው፣ ከነከነው።

ሆዱን በላው 1. አሳዘነው። 2. ከነከነው፣ ቆረቆረው።

ሆዱን ባር ባር አለው ፍርሃት ፍርሃት አለው።

ሆዴ ወዳጄ፣ አንጀቴ፣... ለማለት የሚነገር ቃል።

ሆዴን ጋጠኝ ራበኝ፣ ሞረሞረኝ።

ሆድ ለቀቀበት አልጠግብ አለ፣ ብዙ ምግብ አስፈለገው።

ሆድ ባሰው በትንሽ ነገር ተከፋ፣ አዘነ።

ሆድ የለውም ብዙ አይበላም፣ በትንሽ ምግብ ይጠግባል።

ሆድ ይፍጀው ሆድ ይቻለው፣ ስለሁኔታው መናገር አያስፈልግም።

ሆድና ጀርባ ሆኑ ተቃቃሩ፣ ተቀያየሙ።

በሆዱ/በልቡ አሰበ ሳይናገር በዝምታ አሰበ፣ አሰላሰለ።

በሆዱ አነበበ ድምፅ ሳያሰማ በዝምታ አነበበ።

የሆዱን አውጥቶ ተናገረ ያሰበውን፣ ምስጢሩን አወጣ ወይም ተናገረ።

ሆደ /ልበ ሰፊ ቅ ቻይ፣ ታጋሽ።

ሆደ ቡቡ ቅ 1. አዛኝ፣ ርህሩህ። 2. ሆደ ባሻ።

ሆደ ባሻ ቅ ለማዘን፣ ለማልቀስ ትንሽ ምክንያት የሚበቃው።

ሆደ /ልበ ገር ቅ ርህሩህ፣ የዋህ፣ ገራገር።

ሆዱ/ልቡ አይጠራ ቅ ቂመኛ፣ በቀለኛ።

ሆዱ ዘመዱ ቅ ብቻውን የሚበላ፣ ለሌላ የማያካፍል፣ ንፉግ።

ሆድ ሆዱን ስ ስትጮህ "ሆድ ሆዱን" ያለች የምትመስልና ከሆዷ ዘርጠጥ ያለች ርግብ መሳይ የቆላ ወፍ።

ሆድ ቁርጠት ስ የሆድ ውስጥ ህመም።

ሆድ አምላኩ ቅ ለሆዱ የሚገዛ፣ ስግብግብ።

ሆድ እቃ ስ በሆድ ውስጥ የሚገኙ እንደ ጨጓራ፣ ጉበት፣ አንጀት፣... የመሳሰሉ ብልቶች።

ሆድ ዝማ ስ የተቅማጥ በሽታ።

ሆድ ድርቀት ስ በተገቢው መጠን፣ ጊዜና ሁኔታ አይነምድር (ሰገራ) ከሆድ እንዳይወገድ ችግር የሚያስከትል የሆድ በሽታ።

ሆዳም ቅ ጠገብኩን የማያውቅ፣ ስግብግብ።

ሆጃ ስ በሻይ መልክ ተፈልቶ የሚጠጣ ቁጢ ወይም የቡና ገለፈት።

ሆጭ(ሆጨጭ)

ሆጭ(ሆጨጭ) አለ ግ የጠርሙስ ስብርባሪዎች፣ ሳንቲሞች የመሳሰሉ ነገሮች ሲወድቁ ወይም ሲጋጩ የሚሰሙትን አይነት ድምፅ ሰጠ፣ አሰማ።

ሆጭ(ሆጨጭ) አደረገ ግ 1. አቀረበ፣ ዘረገፈ፣ ሰጠ (ጠገራ ብርን)። 2. ሰበረ፣ አረገፈ(መስተዋትን)።

ኋ "ሀ" ፊደል ፍንዕቅ ዘር።

ኋላ ተው.ግ 1. ቀዮት ብሎ ወይም ወደፊት የሚመጣ ሰአት፣ ጊዜ፣ ወቅት፣ ወዘተ. *ላሁን ልሂድና ኋላ እመለሳለሁ።* 2. በመጨረሻ። *በኋላ ከሚቆጭህ ላሁኑ ጥንቃቄ አድርግ።* 3. ከወደ ጀርባ ያለ ቦታ። *ከእኔ ኋላ ተቀምጦ ነበር።* 4. ታዲያ፣ እንግዲያው። *የማትሰራ ከሆነ ኋላ ለምን መጣህ?*

ኋለኛው ቅ 1.በስተጀርባ በኩል ያለ። 2.ዘግይቶ የመጣ፣ ከአንድ ነገር ቀጥሎ የሆነ። *የኋለኛው ስራ አድካሚ ነበር።*

ኋላቀር ቅ 1. ከጊዜው ሁኔታ ጋር የማይራመድ፣ ጊዜው ያለፈበት። 2. ያልሰለጠነ።

የኋሊት ተው.ግ ወደ ጀርባ፣ ወደ ኋላ አቅጣጫ። *ልጁ የኋሊት ሲሄድ ወደቀ።*

የኋላ ኋላ ተው.ግ ቆይቶ ቆይቶ፣ በመጨረሻ። *የኋላ ኋላ እውነት ማሸነፉ አይቀርም።*

ለ

ለ ከ"ሀ" ፊደል ዘር ቀጥሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል (ግእዙ ሆሄ)።

ለ___ 1. ቀጥተኛ ያልሆነ (ኢርቱእ) ተሳቢ ላይ የሚያርፍና ድርጊት ተቀባዩን የሚያመለክት ምእላድ። *መፅሃፉን ለሰውየው ሰጠሁት*።2.በ___ ላይ፥ በ___ውስጥ። *ገደል ለገደል አትሂድ*። 3. በየ___።*አገር ለአገር ሲዞር ከርሞ መጣ*።4 እና ___ ፡ ___ከ___ጋር። *አህያ ለአህያ ሲራገጥ ጥርስ አይሰበርም*፡ 5. በ___ ምክንያት፡ ለ___ሲል። *ለትምህርት ሄደ /ለሃገሩ ተሰዋ*። 6.አንድን ነገር ለማድረግ፡ ለመስራት፡...። *ለመፃፍ ወረቀት ያስፈልጋል*። 7. ሲካፈል። *አራት ለሁለት ሁለት ጊዜ ይደርሳል*። 8. ሁለት ነገሮች የሚገኙበትን ሁኔታ፡ አቀማመጥ፡ ውጤት፡... በማነፃፀር ለመግለፅ የሚያገለግል ምእላድ። *ፊት ለፊት ተዋውቀዋል /ጎን ለጎን ተቀምጠዋል /ተጋጣሚዎቹ ሁለት ለአንድ ተለያዩ*። 9. ጊዜን ከሚጠቁሙ ቃላት ጋር እየተጣመረ የጊዜውን ርዝመት፡ መጠን፡ ሁኔታ፡... ለመግለፅ የሚያገለግል። *ለነገ፡ ለጊዜው፡ ለመጀመሪያ ጊዜ፡ ለጥቂት ጊዜ፡ ...*።

ለሃጭ ስ እየተንተተ፥ እየተዝረበረበ ከአፍ ውስጥ የሚወጣ ምራቅ፥ ልጋግ።

ለሃጫም ቅ (ስድብ) 1. ሲናገር፡ ሲበላ፡... ምራቁ የሚዝረበረብ። 2. (ዘይ.) ቂላቂል።

ለሆሳስ

በለሆሳስ ተውሳ.ግ. በሹክሹክታ። *በለሆሳስ ተናገረ*።

ለሆቴ ስ ስለት ለማውጣት እንደሞረድ የሚያገለግል ድንጋይ፡ መሳል።

ለመለመ^1 ግ 1. ቅጠል አወጣ፡ አቈጠቈጠ፡ አጀፈጀፈ፥ ጨበጨበ። 2. አረንጓዴ ሆነ፥ ልምላሜ ተላበሰ። *አካባቢው ለምልሟል*።

ለምለም ቅ አረንጓዴ፡ ርጥብ፡ ለጋ። *ለምለም ሳር*።

ለምለም እንጀራ ስ ወጥ ወይም ማባያ የሌለው እንጀራ።

ለምለም ጆሮ ስ ወደታች ያለውና ጉትቻ የሚንጠለጠልበት የጆሮ ክፍል።

ልምላሜ ስ አረንጓዴነት፥ ርጥብ፡ ለጋ፡ ለምለም መሆን።

አለመለመ ግ ለመለመ።

ለመለመ^2 ግ የዛፍን፡ የአትክልትን ቅጠል ወይም ቅርንጫፍ በብዛት ቆረጠ፡ ቀጠፈ፥ መለመለ።

ለመመ ግ አደፈ፥ ንፅህና ከለመጠበቅ የተነሳ ቆሸሸ(ጥርስ፡ ድድ)።

ልማም ስ 1.ቢጫነት ያለውና ጥርስ ላይ የሚታይ ቆሻሻ፡ እድፍ። 2.እርሻ በሚታረስበት ጊዜ በማረሻ ላይ የሚለደፍ ጭቃ።

ለመሰሰ ግ አጋደመ፥ አስተኛ፥ ለሽ አደረገ፥ ለመሸሸ (ሳርን፥ ሰብልን፥...)።

ተለመሰሰ ግ ተኛ፥ ተለሸለሸ።

ለመሸሸ ስ አጋደመ፡ አስተኛ፡ ለሽ አደረገ፡ ለመሰሰ (ሳርን፡ ሰብልን፡...)

ለመሸቀ ግ ራሰ፥ ረጠበ።

ለመነ ግ 1.ችሮታ፡ እርዳታ አድርጉልኝ አለ፥ ምፅዋት ጠየቀ። 2. ፀለየ፡ ተማጠነ። 3. (አንድን ነገር) እባክህ አድርግ ወይም አታድርግ ብሎ ጠየቀ፡ አግባባ።

ለማኝ ስ መንገድ ዳር ተቀምጦ ወይም ከቤት ወደ ቤት በመዘዋወር ጉዳቱን አስተዛዝኖ እየተናገረ ምፅዋት የሚጠይቅ ድሃ፥ የኔ ቢጤ።

ለማኝ ሳያረ በጠዋት፥ በማለዳ። *ለማኝ ሳያረ ተነስቼ ስራዬን ጀመርኩ*።

ልመና ስ 1. ምልጃ፡ ፀሎት። 2. ችሮታ፡ እርዳታ፡ ምፅዋት ጥየቃ።

ልመና አቀረበ ለመነ።

የልመና እህል ስ የተለያዩ የእህል አይነቶች ድብልቅ፥ ሁጥንቅጥ እህል።

ተለመነ ግ 1. ተጠየቀ፥ እባክህ ተባለ። 2. የተጠየቀውን አደረገ፥ ፈፀመ፥ ፈቃድ ሞላ። *መድሃኒአለም ተለምኖኛል*።

ተለማኝ ቅ ርህሩህ፥ እሺ ባይ። *አምላካችን እግዚአብሔር ተለማኝ ነው*።

ተለማመነ ግ ዛሩን ወይም ውቃቢን ለመነ፥ ተለማመጠ።

መለማመኛ ስ ለተለማኙ ዛር ወይም ውቃቢ የሚቀርብ ስጦታ፥ ምስ።

አለመነ ግ ለጠየቀ ወይም ለለመነ ሰው ሰጠ፥ ቸረ።

አስለመነ ግ ደጅ አስጠና፡ ብዙ ተለመነ።

ለመከከ ግ ቀባ፡ ላከከ።

*ለመዘመዘ

ተለመዘመዘ ግ ታሸ፡ ተፍተለተለ።

አለመዘመዘ ግ አሸ፥ አፍተለተለ።

ለመዘገ(መዘለገ) ግ በሃይል አጥብቆ ቆነጠጠ።

ለመደ ግ 1. አብሮ ከመቆየት ወይም ከማዘውተር የተነሳ የአንድን ነገር ጠባይ፣ ሁኔታ፣ አሰራር፣...አወቀ። *ስራውን ለመደው።* 2. አንድን ነገር መስራት፣ ማድረግ ተማረ፣ ሰለጠነ። *መኪና መንዳት ለመደ።* 3. ከአካባቢው ጋር ተስማማ፣ ተዋወቀ። *አገሩን ለመደው።* 4. አዘወተረ፣ ደጋገመ። *የስራ ሰዓት ማሳለፍ ለመደ።* 5. አመል አወጣ፣ ሱሰኛ ሆነ። *መጠጥ ለመደ።* 6. ለዘበ፣ ገራም ሆነ። *ላሚቱ እያደር ለመደች።*

እንዳይለምድህ ሁለተኛ፣ ዳግመኛ እንዳታደርግ።

ለማዳ(ለማድ) ቅ 1. ገራም፣ በተፈጥሮ የነበረውን የአውሬነት፣ የበርጋጊነት ባህርይውን የተወ። 2. በቀላሉ የሚለምድ።

ለማጅ ቅ 1. አንድን ነገር በመስራት ወይም በማድረግ ለማወቅ በመማር ላይ ያለ። 2.አንድን ነገር መስራት፣ ማድረግ፣ ...ጠንቅቆ የማያውቅ፣ ጀማሪ።

ልማድ ስ 1. ዘወትር በተደጋጋሚ የሚደረግ፣ የሚሰራ። *ስፖርት የመስራት ልማድ አለኝ።* 2. ሱስ። *የመጠጥ ልማድ አለበት።* 3. ባህርይ፣ አመል። *መሳደብ ልማዱ ነው።* 4. ዘወትር፣ በተደጋጋሚ በመስራቱ ወይም በመደረጉ እንደ ደንብ፣ እንደ ህግ የተወሰደ። *በጠዋት መነሳቱን እንደ ልማድ ይዞታል።* 5. አንድ ማህበረሰብ የሚከተለው፣ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ የመጣ ወግ፣ ስርአት፣ ባህል።

በዘልማድ ተው.ግ. በተለምዶ።

እንደልማዱ በዚህ ቀደም ሲያደርግ እንደነበረው።

ልማደኛ ቅ (ብዙውን ጊዜ መጥፎ ድርጊትን) በተደጋጋሚ የሚፈፅም፣ የሚያደርግ።

ልማዳዊ ቅ የተለመደ፣ ያልተለወጠ፣ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ። *ልማዳዊ የአስተራረስ ዘዴ።*

ልምድ ስ 1. ከማየት፣ ከመስማት፣ ከማድረግ፣... የሚገኝ እውቀት፣ ግጠመኝ። *ካለፈው ስራ ጥሩ ልምድ አገኘ።* 2.በማዘውተር የሚፈፀም ድርጊት። *ከእንቅልፌ ጠዋት የመንቃት ልምድ አለኝ።*

የልምድ ልውውጥ ስ በስራ ሂደት ውስጥ የተገኘን እውቀት ለሌላ ማካፈልና በአንፃሩም ሌላው ካገኘው ልምድ መማር።

መልመጃ ስ እውቀትን፣ ብቃትን፣ ችሎታን ለማየት የሚሰጥ የሙከራ ጥያቄ።

ልምምድ ስ የችሎታ ብቃትን ለማግኘት በተደጋጋሚ የሚደረግ ክንውን።

ተለመደ ግ በመዘውተሩ ወይም በመደጋገሙ የተነሳ አዲስ ወይም እንግዳ መሆኑ ቀረ።

አይለመድም 1.ሊለመድ ባለመቻሉ ሁልጊዜ አዲስ፣ እንግዳ ነው። *ሞት አይለመድም/ስራው ከባድ ነው፣ በቀላሉ አይለመድም።* 2.ሁለተኛ አይደገምም። *እንዲህ አይነት ጥፋት አይለመደንም።*

እንደተለመደው ከዚህ በፊት እንደሚደረገው፣ እንደሚሰራው፣ እንደሚታወቀው።

በተለምዶ ተው.ግ. በነበረው፣ በቆየው ልማድ፣ ወይም ስርአት መሰረት ፤ በዘልማድ። *ጊዜ የፈጠረው ሳይሆን በተለምዶ ሲደረግ የቆየ ነው።*

ተለማመደ ግ 1. አንድን ነገር በጥራት ወይም በብቃት የማከናወን ችሎታ ለማግኘት አስፈላጊውን ልምምድ አደረገ። *መኪና መንዳት እየተለማመድኩ ነው።* 2. አንድን ነገር በጥራት ወይም በብቃት የማከናወን ችሎታ አገኘ። *ቢስክሌት መንዳት ተለማምዷል።*

መለማመጃ ስ ሙከራ ማድረጊያ ጊዜ፣ ስፍራ፣ እቃ።

ተለማማጅ ቅ በልምምድ ላይ ያለ (ሰው)።

ተላመደ ግ 1. ተቀራረበ፣ ተግባባ። *ላብረውት ከሚሰሩት ሰዎች ጋር ተላመደ።* 2.እየቻለ፣ እያወቀ መጣ። *አዲሱን ስራ ተላመደው።* 3. የ"**ለመደ**"ን ሶስተኛ ፍቺ ተመ.

አለመደ ግ ገራም፣ ለማዳ አደረገ።

አለማመደ ግ 1. አስተማረ፣ አሰለጠነ፣ አሳወቀ። *መኪና መንዳት አለማመደ።* 2.አላመደ፣ እንግዳነት እንዳይሰማው ከእንግዳው ጋር አብሮ ሆነ።

አለማማጅ ስ አሰልጣኝ።

አላመደ ግ እንግዳውን ከአካባቢው ጋር አስተዋወቀ፣ አብሮ በመሆን ብቸኝነት እንዳይሰማው አደረገ።

አስለመደ ግ 1. አስተማረ፣ አሳወቀ፣ አሰለጠነ። 2. ሱሰኛ፣ ልማደኛ አደረገ (የሲጋራ፣ የመጠጥ፣...)።

ለመገገ[1] ግ ሳበ፣ መጠመጠ፣ ጠባ (ጡትን)።

ለመገገ[2] ግ ጎፈነነ፣ ጎመዘዘ።

ለመጠ[1] ግ 1. አጎበጠ፣ አስጎነበሰ። 2. በዱላ መታ፣ ጠለዘ፣ ገሰለጠ። 3. ረግጦ ገዛ። *አምባገነኑ መሪ ህዝቡን ለምጦ ገዛው።*

ምን ይለምጥሃል ምን ይለጥጥሃል፣ ምን ይጀንንሃል፣ ምን ያኮራሃል።

ለማጣ ቅ 1. በቀላሉ የሚጎብጥ፣ የሚታጠፍ። 2. አቅመቢስ፣ ልፍስፍስ። 3. (ዘይ.) ጠንካራ አቋም የሌለው፣ ባህርየ ደካማ።

ልምጭ ስ አርጩሜ፣ ለበቅ።

ልምጭ አይነካሽ ስ ጡንቻ ወይም ነብር።

ለመጥማጣ ቅ 1. ለማጣ። 2. ተለማማጭ።

ልምጥምጥ ዝ.ከ.

ተለመጠ ግ ታጠፈ፡ ጎበጠ።

ተለማመጠ ግ በትህትና ለመነ፡ አግባባ፡ አባበለ።

ተለማማጭ ቅ ከመፍራት፡ አቅም ከማጣት፡... የተነሳ ሌላውን የሚለምን።

ተልመጠመጠ ግ 1. ሰውነቱ ረገደ፡ ተብረከረከ፡ አቅም አጣ። 2. የሚታጠፍ አይነት ሆነ፡ ረገብ ረገብ አለ። 3. እየተቅለሰለሰ ለመነ፡ አግባባ፡ አባበለ።

አለማመጠ ግ ደጅ አስጠና፡ አሽቆጠቆጠ። *ለማይሆን ነገር ምን አለማመጠው።*

ለመጠ² ግ እህልን በምጣድ አመሰ፡ ሞቅ ሞቅ አደረገ።

ለመጠ¹ ግ ምላጩን በጠፍር ሳለ ወይም ሞረደ።

ለመጠ⁴ ግ በብዛት ጠጣ። *ጠላውን ሲለምጥ ዋለ።*

***ለመጠ**

ልሙጥ ቅ ሸንተረር፡ መስመር፡ ስንጥር፡ ጥልፍ፡ ሽልማት፡ ጌጥ፡ ...የሌለው አንድ ወጥ የሆነ መልክ የያዘ፡ ልስልስ።

ልሙጥ ሸማ ስ ጥለት የሌለው ሸማ።

ልሙጥ ብርሌ ስ ሽልማት ሸንተረር የሌለው ብርሌ።

ልሙጥ ወረቀት ስ መስመር የሌለው ወረቀት።

ልሙጥ የበቅሎ እቃ ስ ቆዳው ላይ ሽልማት ወይም ሸንተረር የሌለው የበቅሎ እቃ።

ልሙጥ ጥለት ስ ጥበብ ያልሆነ ጥለት

ልሙጥ ጨርቅ ስ የሃረግ፡ የአበባ፡... ዲዛይን ያልተሳለበት አንድ መልክ የሆነ ጨርቅ።

ለመጠጠ¹ ግ 1. ፈጀ፡ አቃጠለ። 2. ገረፈ፡ ሸነቆጠ።

ለመጠጠ² ግ ለጥ አደረገ፡ አስተኛ።

ልምጥጥ አለ ግ 1. ተኛ፡ ለጥ አለ(ሀገር)። 2. አይን የሌለው ወይም ልሙጥ ሆነ (እንጀራ)።

ለመጨቀ ግ 1. ላቆጠ፡ ሞቀሞቀ። 2. ጨቀየ፡ ጭቃ ሆነ።

ለመጨጨ ግ 1. አስተኛ፡ ለሽ አደረገ (ፀጉርን በቅባት)። 2. ተኛ፡ ለሽ አለ (ቅባት የበዛበት ፀጉር)። 3. ሞቀሞቀ፡ ጭምልቅ አለ።

ለማ ግ 1. ለመለመ፡ ፀደቀ (ተክል)። 2. ቀና፡ ሰመረ፡ በእርሻ ዳበረ (መሬት)። 3. አደገ፡ በለፀገ (በኢኮኖሚ፡ በኢንዱስትሪ፡...)። *አገሩ ለምቷል።* 4. በጀ፡ ጠቀመ። *ከፋም ለማም እሱ ይሻላል።* 5. ነደደ፡ ተቀጣጠለ (እሳት)። 6. ዳበረ፡ ወፈረ። *ሰውነቱ ለምቷል።*

በመልማት ላይ ያሉ አገሮች ስ በአፍሪካ፡ በላቲን አሜሪካ፡ በእስያ የሚገኙና ኋላ ቀር ኢኮኖሚያቸውን ለማሳደግ ጥረት በማድረግ ላይ ያሉ አገሮች።

የለሙ አገሮች ስ በኢኮኖሚ፡ በቴክኖሎጂ፡... የበለፀጉ ወይም ያደጉ አገሮች።

ለም ቅ 1. የቀና፡ ምርታማ (መሬት)። 2. ቢታረስ ጥሩ ምርት ሊሰጥ የሚችል (መሬት)።

ለም ከጠፍ ቅ 1. በከፊል የቀና በከፊል ያልቀና (መሬት)። 2. በከፊል ብቻ መልማት የሚችል (መሬት)።

የለም ጠፍ መሬት ስ በተፈጥሮው ለም ሆኖ ሳለ ያልታረሰ መሬት።

ልማት ስ 1.ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት፡ ብልፅግና፡ ግንባታ። 2. ጥሩ፡ መልካም ተግባር። *ከልማት ጥፋቱ።*

አለማ ግ 1. (መሬትን፡ አካባቢውን)አርሶ፡ ዘርቶ አበቀለበት። 2. በኢኮኖሚ አሳደገ፡ አዳበረ።

አልሚ ምግብ ስ ለአካል ግንባታና ለእድገት የሚበጅ ምግብ።

ለማኝ "**ለመነ**" ስር ተመ.

ለማዳ "**ለመደ**" ስር ተመ.

ለምለም "**ለመለመ**¹" ስር ተመ.

ለምባዳ "**ለንባዳ**" ን ተመ.

ለምቦጭ "**ለንቦጭ**" ን ተመ.

ለምድ ስ 1. ከግምጃ ወይም ከሃር ወይም ከተለፋ የአንበሳ ወይም የነብር ወይም የግስላ ቆዳ ተሰፍቶ የተዘጋጀ የቀድሞ የጦር አለቆች የሚለብሱት የማእረግ ልብስ፤ ወይም ከግምጃ፡ ከሃር የተዘጋጀና በበአል ቀን ዲያቆናት የሚለብሱት የቤተክርስቲያን ልብስ። 2. ከበግ ወይም ከፍየል ቆዳ የሚዘጋጅ ገበሬ ወይም እረኛ የሚለብሰው ደበሎ።



ለምድ

ለምድ ለበስ ማድረግ የሚገባውን ባለማድረጉ (ለምሳሌ ለቅሶ ባለመድረስ) አፈረ።

ለምድ አወጣ ለምድ እንዲሆን አድርጎ የበግ ቆዳን ገፈፈ።

ለምፅ (ለምጥ) ስ የቆዳን የተፈጥሮ ቀለም ለውጦ ነጭ የሚያደርግ የቆዳ በሽታ።

ለምፃም ቅ ለምፅ ያለበት (ሰው)።

ለሰለሰ ግ 1. ተልጎ ወይም ተፍቆ ሻካራነቱን ተወ፤ ለዘበ። 2. ላመ። 3. ተደጋግሞ ታረሰ።

እርግጫው ለሰለሰ:: 4.ሃይሉን፡ ኩስታራነቱን ቀነሰ:: *ጠባው ለሰለሰ::* 5. ሃይለኛነቱን ተወ፣ ገራም ሆነ (ለጠባይ)::

ለስላሳ ቅ 1. የማይሻክር፡ ልዝብ:: 2. ሃይል የሌለው፡ የማያስከር የአልኮል መጠጥ::

ለስላሳ [መጠጥ] አልኮልነት የሌለው ጣፋጭ የሆነ መጠጥ::

ለስላሳ ሙዚቃ ስ ፍጥነት ያልበዛበት፡ ዝግ ያለ ምት ያለው የሙዚቃ ቅንብር::

ልስልስ ቅ 1. ሻካራነት የሌለው፡ ከርዳዳ ያልሆነ:: 2. (ዘይ.) ለሰው ጥሩ የሆነ:: *እገሌ ለሰው ልስልስ ነው::*

ተለሳለሰ ግ 1. ተቅለሰለሰ:: 2. ስራ ተወ፡ ተቀምጦ ዋለ:: 3. ይዞት የነበረውን ጠንከር ያለ አቋም (አመለካከት፡ ጥያቄ፡ ውሳኔ፡...) ለዘብ አደረገ፡ በረድ፡ ቀዝቀዝ አለ::

አለሰለሰ ግ ባዘተ፡ በጨቀ (ጥጥን)::

አለሳለሰ ግ 1. አሻሸ፡ ያዝ ተወት አደረገ (ህመምን):: 2. ቀስ፡ ረጋ፣ ለዘብ አደረገ:: *ችግሩን ለሃላፊው አለሳልሶ ነገረው::* 3. ላላ፡ ረገብ አደረገ (ግትር አቋምን)::

ለሰሰ ግ ለብ አለ፡ በጥቂቱ ሞቀ (ውሃ)::

ለስስታ ስ መጠነኛ ሙቀት፡ ለብታ::

ለስታ ዝ.ከ.

ለስታ ቅቤ ስ 1. ከወተት መናጫው ወዲያው የወጣ ትኩስ ቅቤ:: 2. ያልተነጠረ ቅቤ::

ለሰስ አለ ግ ለብ፡ ሞቅ አለ (ውሃ)::

ለስ አለ ዝ.ከ.

ለሰቀ ግ 1. እንዲጠጋ፡ ሰጥ ቀጥ ወይም ልክክ እንዲል ተደረገ ወይም አደረገ:: *ወረቀቱን ለስቀህ አስረው::* 2. ተጠጋ፡ ልክክ አለ::

ልስቅ አለ ግ ልክክ፡ ልጥቅ አለ፡ ተጠጋ::

ተለሰቀ ግ ተያያዘ፡ ተጣበቀ፡ ተጠጋጋ::

ለሰነ ግ ልጥፍን፡ ምርግን ላላ ባለ ጭቃና ጭድ እየቀባ ተመተመ፡ ለቀለቀ፡ አባጣ ጎባጣውን አስተካከለ::

ለሰንበት በጥፊ መታው::

ለሳኝ ስ የመለሰን ስራ የሚሰራ ባለሙያ::

ልስን ስ 1.ልጥፉ በጭድና ላላ ባለ ጭቃ በመለሰኛ የተስተካከለና የለሰለሰ ምርግ:: 2.የመለሰን ስራ:: *የቤቱ ምርግ ልስን ይቀረዋል::*

መለሰኛ ስ ለልስን ስራ የሚያገለግል ጠፍጣፋ እንጨት::



መለሰኛ

ለሴ ስ ለከት፣ ሙልሙል፣ ጥቢኛ::

ለሸለሸ ግ ጣለ፣ አጋደመ፡ አስተኛ፡ ረፈረፈ::

ለሽ አለ ግ ተኛ፡ ተጋደመ፣ ወደቀ::

ተለሸለሸ ግ ተኛ፣ ተጋደመ፣ ተረፈረፈ::

ለቀለቀ ግ 1. ቀባ (በቅባት ወይም በቀለም፡ ወይም በእበት፣...):: 2. በሳሙና ወይም በአሞ፣ ወይም በእንዶድ፡...የታሸውን በውሃ አጠራ:: 3. አጠበ፣ አፀዳ:: 4. በብዛት ወይም በስፋት ሰራ፣ ገነባ (ቤትን፡ ድንኳንን፣ ...):: 5. ፃፈ (በብዛት)::

ልቅላቂ ስ 1. እጣቢ:: 2.(ዘይ.፡ ስድብ) የማይረባ፡ ተልካሻ፡ ልክስክስ::

ተለቃለቀ ግ 1.ተጣጠበ:: 2. (ዘይ.) ተነካካ፡ አንዱ ሌላውን በከለ:: (ለምሳሌ በነገር)::

አለቀለቀ ግ አጠበ፡ በውሃ አጣራ::

አለቅላቂ ቅ (ዘይ.፣ ስድብ) አጎብዳጅ፡ አወደድ ባይ፡ አሳባቂ::

አለቃለቀ ግ አነካካ፡ በከለ:: (ለምሳሌ በነገር)::

ለቀመ ግ 1. አነሳ፡ ብድግ ብድግ አደረገ:: 2. ሰበሰበ:: *ማገዶ ለቀመ::* 3. ፊደሎችን በተገቢ ቦታቸው በመደርደር ለህትመት አዘጋጀ (ማተሚያ ቤት):: 4. ለየ፣ ነቀሰ:: *ከስንዴ ውስጥ የተደባለቀውን በቆሎ እየለቀመ አወጣ::* 5. የመጻፍ ልቅም ጥበብ ሰራ:: 6. ሳር ጋጠ፣ በላ:: *በጎቹ ሳር ይለቅማሉ::* 7. በላ:: *የተዘራውን ወፍ ለቅሞ ጨረሰው::* 8. ያዘ:: *በከተማው ውስጥ ያሉትን ሌቦች ፖሊሶች ለቀሟቸው::* 9. ገደለ፣ ፈጀ፡ ጨረሰ:: *ጠላቶቹን በጥይት ለቀማቸው::*

ለቀም (ለቅም) ስ ግጦሽ::

ልቃሚ ቅ 1. ከእህል ውስጥ ተለይቶ የሚወጣ ጉድፍ፣ ብጣሪ:: 2.(ዘይ.፣ ስድብ) የማይረባ ልክስክስ፡ ተልካሻ፡ ጥርቃሚ::

ልቃሞ ዝ.ከ.

ልቅሞሽ ስ ልጆች አምስት ወይም ሰባት ጠጠር ይዘው ሽቅብ እየወረወሩና እየቀለቡ የሚጫወቱት ጨዋታ፣ ቅልቦሽ::

መልቀሚያ ስ በሽማ ጥበብ ስራ ጊዜ ሃሩን (ጥለቱን) ለማወሳሰብ የሚያገለግል ከወደ ጫፉ ሾል ያለ ጥርብ እንጨት ወይም ሸንበቆ::

ለቀም አደረገ ግ ያዘ፣ አፈፍ አደረገ::

ለቃቀመ ግ ምንም ሳይቀር ሁሉንም ያዘ፣ ወሰደ::

ለቃቃሚ ቅ (ስድብ) ልክስክስ::

ልቅምቃሚ ቅ 1. ትርፍራፊ፡ ጥርቅምቃሚ፡ የወዳደቀ:: 2. (ዘይ፣ ስድብ) የማይረባ፣ ተልካሻ::

ልቅምቅም (ልቅምቃሞ) ዝ.ከ.

አለቀመ ግ ሳር አጋጠ፣ አበላ (ከብቶችን)።

*ለቀሰ

ለቀስተኛ ስ የሬሳ አጃቢ፣ ለቅሶ የሚደርስ፣ የሚያስተዛዝን ሰው።

ለቅሶ (ልቅሶ) ስ 1. ሃዘን። 2. ሙሾ፣ ዋይ ዋይታ። 3. መሮሁ፣ ማንባት። 4. የእንባ መመንጨት፣ መውረድ፣ መፍሰስ።

ለቅሶ ተቀመጠ ዘመድ ወይም ወዳጅ ስለሞተበት ሃዘን ላይ ሆነ (በተወሰነ ቦታ ተቀምጦ አስተዛዛኞችን ወይም ለቅሶ ደራሾችን ለመቀበል)።

ለቅሶ ደረሰ ዘመድ ወዳጅ የሞተበት ሰው ዘንድ ሄደ (ለማስተዛዘን)።

ለቅሶ ቤት ስ ለቅሶ ወይም ሃዘን ያለበት ቤት (ሰው በመሞቱ ምክንያት)።

ለቅሶኛ ስ ለቀስተኛ።

ተለቀሰ ግ እንባ በማፍሰስ፣ በመጮሁ፣ ዋይ ዋይ በማለት ታዘነ፣ ሃዘን ተገለፀ።

መለቀሻ ስ በለቅሶ ጊዜ ሟች እየታወሰ የሚለቀስበት የሟች ምስል፣ አገበር፣ ፎቶግራፍ፣ የሟቹ የማእረግ ልብስ፣ ወዘተ.

ተለቃሽ ስ የሟች ቤተዘመድ።

ተላቀሰ ግ 1. በአንድነት ተሰባስቦ በእንባ ሃዘኑን ገለፀ። 2. ተማረረ፤ እሮሮ አሰማ።

አለቀሰ ግ 1. በሃዘን፣ በብስጭት፣ በደስታ፤...ስሜቱ ስለተነካ እንባውን አፈሰሰ፣ አነባ። 2.እንባ አፈሰሰ (አይን በጭስ፤ በህመም፣... ምክንያት)። 3. አማረረ፣ እሮሮ አሰማ።

ማልቀሻ ስ መለቀሻ።

አልቃሻ ቅ ነጭናጫ፣ ሆደባሻ፣ በሆነ ባልሆነ ነገር የሚያለቅስ።

አልቃሽ ስ 1. ለቀስተኛ። 2. በለቅሶ ጊዜ ሙሾ በማውረድ የሚያስለቅስ ሰው (ብዙውን ጊዜ ሴት)።

አልቃሽ ቆመ ሙሾ እያወረደና የሟችን ስም በግጥም እያነሳ ሃዘንተኞችን ለማስለቀስ አልቃሹ በለቅሶ መካከል ተገኘ።

አለቃቀሰ ግ ተነጫነጨ።

አላቀሰ ግ ከሟች ቤተሰብ ጋር አብሮ አለቀሰ፣ አስተዛዘነ።

አስለቀሰ ግ 1. እንዲያለቅስ፣ እንባ እንዲያፈስ አደረገ። 2. ሙሾ በማውረድ እንዲለቀስ አደረገ። 3. አበሳጨ፣ አስከፋ።

ማስለቀሻ ስ መለቀሻ።

አስለቃሽ ስ የ "**አልቃሽ**" 2ኛ ፍቺን ተመ.

አስለቃሽ ጋዝ ስ እንባ አስመጪ ጋዝ።

ለቀቀ ግ 1. ተወ። *በሽታው ለቀቀው።* 2. ነፃ አደረገ፣ ፈታ። *እስረኞቹን ለቀቃቸው።* 3. ፈታ፤ ሰደደ፤ አሰማራ። *ከብቶቹን ለቀቃቸው።* 4. (መኖሪያን፣ መስሪያ ቤትን፣ ...) ትቶ ሄደ። 5. ጠፋ፣ ተወገደ። *ብርዱ ለቀቀ።* 6. መረን ሰደደ፣ ያለ ቁጥጥር ተወ። 7. ተተረተረ። *ስፌቱ ለቀቀ።* 8. (የተጣበቀው፣ የተያያዘው፣ ...) ተለያየ። 9.(ቀለሙ፤ መልኩ፤ ...) ቀየረ፤ ደበዘዘ፣ ጠፋ። 10. (ቆሻሻው) ተወገደ። 11. ዋጋ ቀንሶ ሸጠ። 12. አንድን ድርጊት በስፋት፤ በብዛት፣ ያለገደብ ወይም ከቁጥጥር ውጪ በሆነ መንገድ አከናወነ፤ ፈፀመ። *ጩሀቱን/ሳቁን ለቀቀው።* 13. ጥጥን ፈትሎ ልቃቂት አወጣ፣ አለቀቀ።

ሊቃቃ ቅ ሰፊ። *ሊቃቃ ቤት /አፈ ሊቃቃ እንስራ።*

ልቃቂት (ልቅ) ስ ጥጥን በመፍተል እንዝርቱ ከሞላ በኋላ የሚወጣው ማግ፤ ፈትል።

ልቅ ቅ 1. ሰፊ። *ላዳራሹ ልቅ ነው።* 2. ስድ፣ ባለጌ። ስ 3. "**ልቃቂት**"ን ተመ.

ልቅ ወጣ 1.ሙልጭ ወጣ፣ ምንም ሳይከፈል፣ ሳያገኝ፣ ሳይዝ ባዶ እጁን ቀረ። 2. ስድ፤ ባለጌ ሆነ፣ ተቆጣጣሪ አጣ።

ልቅ ቀሚስ ስ ወገቡ ላይ ሽንሽን የሌለው ሰፊ ቀሚስ።

መልቀቂያ ስ መሰናበቻ ደብዳቤ (ከስራ፣ ከትምህርት)።

ተለቀቀ ግ 1. ተፈታ (እስረኛ)። 2.ባዶ፣ ነፃ ሆነ (ቤት)። 3. ተተወ፣ ቀረ (እገዳ)።

ተለቀቀበት 1. (በብዛት፣ በስፋት) ተሰማራበት፣ ፋሽን አድርጎ ያዘው።*በሆቴል ንግድ ሰዉ ተለቀቀበት/ በአዲሱ ፋሽን ልብስ ሰው ሁሉ ተለቀቀበት።* 2. በብዛት ታየ፣ ተከሰተ። *በለፋ በሽታ ተለቀቀበት።* 3. ስድብ አወረደበት።

ተላቀቀ ግ 1. ተለያየ፤ ተነጣጠለ፤ ተገነጠለ። 2. አረፈ፣ ተገላገለ፣ ነፃ ሆነ።

መላቀቂያ ስ መጋጠሚያ (ለሰውነት ክፍል)።

አለቀቀ ግ የ"**ለቀቀ**"ን 13ኛ ፍቺ ተመ.

አላቀቀ ግ 1. ለያየ፣ ነጣጠለ። 2. አፋሸገ፣ አዘጋ። 3. ገላገለ።

ማሳቀቂያ ስ ሁለት ነገሮችን ለመለያየት የሚረዳ ነገር ወይም መሳሪያ።

አስለቀቀ ግ 1. ነፃ አወጣ። *ምሽጉን አስለቀቀ።* 2. አስወጣ። (ለምሳሌ ተከራዩን ከቤት)። 3. አፀዳ፥ ንፁህ አደረገ። 4. አስመለሰ (ተይዞበት የነበረውን)። 5. ርኩስ መንፈስን በፀሎትና በጠበል በማስወጣት የታመመውን አዳነ፥ ፈወሰ።

ማስለቀቂያ ስ 1.ማስጣያ። 2. ማስወገጃ። 3.ማስመለሻ (ተይዞ የነበረውን)። 4.ማስፈቻ። 5. ማፅጃ።

ለቀተ ግ አበደረ፥ አለቀተ።

ተለቀተ ግ ተበደረ።

አለቀተ ግ አበደረ፥ ለቀተ።

***ለቃ**

ልቆ ስ ብድር።

ልቆኛ ቅ ተበዳሪ፥ ሁልጊዜ ከብድር የማይወጣ።

ተለቃ ግ ተበደረ።

አለቃ ግ አበደረ።

ለቅም "**ለቀመ**" ስር "**ለቀም**" ን ተመ.

ለቅሶ "**ለቀሰ**" ስር ተመ.

ለቆ ስ 1. ከበጋ ቀጥሎ የሚመጣ የበልግ ወቅት። 2. በበልግ ወቅት የሚበቅል ለምለም ሳር። 3.ከድርቅ በኋላ የሚበቅል ለምለም ሳርን የበላ ከብት ቅዘን።

ለቆታ ስ ስልቻ፥ ቀልቀሎ።

ለበለበ ግ 1. በእሳት ጠበሰ፥ አሞቀ። *ምሬቱን ለማረቅ በእሳት ለበለበው።* 2.አቃጠለ፥ ፈጀ (ቃሪያ፥ በርበሬ፥ ሳማ፥ ...)። 3. መታ፥ ገረፈ፥ ሸንቆጠ (በአርጩሜ፥ በለበቅ፥ በአለንጋ፥ ...)። 4. ቆጠቆጠ፥ አመመ፥ አንጣጣ (ቁስል)። 5. ነዘነዘ፥ ጨቀጨቀ፥ ነተረከ፥ አንገበገበ (በነገር)። 6. (የአራዳ አነ.) በብዛት ጠጣ (አልኮልን)። 7. አንድን ድርጊት በብዛት አከናወነ። *ጥናቱን ሲለበልብ ዋለ።*

ለብላቢ ቅ (የአራዳ አነ.) ጠጪ፥ ሰካራም።

መለብለቢያ ስ ቀጭን የመቀነቻ ጠፍር፥ መጥለፊያ፥ ማሰሪያ።

ተለባለበ ግ አቃጠለ፥ ተፋጀ (ቃሪያ፥ በርበሬ፥ ...)።

አለብላቢት (ለብላቢት) ስ 1. ሲነኩት እንደ ሳማ የምታቃጥል እፅ። 2. (ዘይ.፥ ስድብ) ምላሰኛ፥ ለፍላፊ።

ለበሰ ግ 1. ሸፈነ (ሰውነቱን በልብስ፥ በቆዳ፥ ...)። 2. ተሸፈነ። *አካባቢው ጉም ስለ ለበሰ ከሩቅ ማየት አይቻልም።* 3. ጠጣ፥ ከለበሰ። *ሁለት ብርሌ ጠጅ ከለበሰ ሰው አያናግርም።*

ለብሰህ ፍጀው አዲስ ልብስ የለበሰን ሰው ልብሱን ለብሰህ ጨርሰው ለማለት የሚነገር ምርቃት።

ለባሽ ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) የእለቱ ተረኛ ቀዳሽ።

ልባስ ስ ሽፋን፥ መሸፈኛ።

ልብስ ስ ከሃር፥ ከፀጉር፥ ከጥጥ፥..የሚሰራ የሰውነት መሸፈኛ

ልብስ አስቀደደ/አስለካ ልብስ ለማስፋት በልኩ አስቆረጠ።

ልብሰ መንግስት ስ ንጉስ በዙፋን ሲቀመጥ የሚለብሰው የማእረግ ልብስ።

ልብሰ ማርያም ስ በሰማያዊና በቀይ ከፋይ ቀለም የሚሳል የማርያም ስእል ካባ።

ልብሰ ተክህኖ ስ በመንፈሳዊ አገልግሎት ጊዜ ቀሳውስትና ዲያቆናት በቤተክርስቲያን የሚለብሱት ልብስ።

ልብስ መስቀያ ስ ከብረት፥ ከእንጨት፥ ... የሚሰራ የልብስ ማንጠልጠያ።

ልብስ ሰፊ ስ እንደ ኮት፥ ሸሚዝ፥ ቀሚስ፥ ... ያሉ ልብሶችን በልብስ ስፌት መኪና እየሰፋ የሚተዳደር ባለሙያ።

ልብስ አጣቢ ስ ልብስ በማጠብና በመተኮስ በሚያገኘው ገቢ የሚተዳደር ሰው።

የልብስ ሳሙና ስ በተለይ ለልብስ ማፅጃ ወይም ማጠቢያ እንዲያገለግል የተዘጋጀ ሳሙና።

የልብስ ንፅህና መስጫ ስ በዘመናዊ የልብስ ማጠቢያ መሳሪያ ልብሶችን የሚያጥብ ወይም የሚያፀዳ ድርጅት፥ ላውንድሪ።

ልብስ (ልባሽ) ስ አዲስ ያልሆነ፥ የተለበሰ ልብስ፥ ውራጅ።

መልበሻ ክፍል ስ ለተወሰነ ስራ አስፈላጊ የሚሆነው የሙያ ልብስ የሚቀየርበት ክፍል (ለምሳሌ ቲያትር ቤት ውስጥ፥...)።

ለበስ አለ ግ ወፈር አለ።

ተለባበሰ ግ 1.ተድበሰበሰ፥ ተሸፋፈነ። 2.አንዱ የሌላውን ምስጢር ወይም ገመና ሸሸገ፥ ደበቀ።

ተላበሰ ግ 1. ኩታውን መስቀለኛ ለበሰ፥ አደገደገ (ካህን፥ ዲያቆን፥ ...)። 2. ተዋሃደ። *ተዋናዩ የሚወክለውን ገፀባህርይ ተላብሶታል።* 3. አገኘ። *ግርማ ሞገስ ተላበሰ።*

አለበሰ ግ 1. በብዛት ሸፈነ። *አዝመራው አገሩን አልብሶታል።* 2. ልብስ ሰጠ፥ ገዛ። *አጎቴ ለጥምቀት አዲስ ልብስ አለበሰኝ።*

አልብሺኝ አንተርሺኝ የጣጣ ብዛት፥ ሰበብ አስባብ። *የዛሬው ቀን በአልብሺኝ አንተርሺኝ መሸ።*

አልባሽ ስ (ለንጉስ፣ ለልእልት፣...) ልብስ የሚያቀርብ፣ የሚያለብስ ባለሟል።

አለባበሰ ግ 1. ነካ ነካ አድርጎ ተወ፣ በሚገባ ሳይሰራ ቀረ። *ላለባበሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ።* 2. አድበሰበሰ፣ ሸፋፈነ፣ ግልፅ እንዳይሆን አደረገ።

ማላበሻ ስ አላባሽ።

አላባሽ ስ አብሮ የሚለበስ፣ ማሟያ ልብስ። *ሱሪው ላባሽ ኮት የለውም።*

ለበቀ ግ 1.ለማስታወክ ወይም ለማስመለስ ተናነቀ። 2. አስታወከ፣ አስመለሰ።

ለበቅ ስ መግረፊያ ነገር፣ ጠንገር፣ አርጩሜ፣ ልምጭ።

ለበን^{1} ስ ለምቦጭ፣ የታችኛ ከንፈር።

ለበኑን ጣለ አኮረፈ።

ለበናም ቅ (ስድብ) ለምቦጫም።

ለበን^{2} ስ የጠመንጃ አይነት።

ለበደ ግ 1. የአንድን ነገር አካል በቆዳ፣ በወርቅ፣... ሸፈነ፣ ጠረዘ፣ አሸገ። *ጉድጓዳውን በጋዜጣ ለበደ።* 2. ሽንቁርን ወይም ቀዳዳን ደፈነ፣ ሸፈነ።

መለበጃ ስ መሸፈኛ (የደብተር፣ የመፅሃፍ)።

ለበጠ ግ በመፅሃፍ፣ በጋሻ፣ ... ላይ ብርን፣ ወርቅን በመለጠፍ አስጌጠ፣ አስዋበ።

ለበጣ ስ ሽሙጥ፣ ሽርደዳ፣ ምፀት።

የለበጣ ስራ ስ ከልብ ያልሆነ፣ የልግም ስራ።

ለብ

ለብታ ስ 1. መጠነኛ ሙቀት፣ ለስላሳ (የውሃ)። 2. (ዘይ.) ሞቅታ፣ መጠነኛ ስካር።

ለብታ ውሃ ስ ሞቅ፣ ለሰስ ያለ ውሃ።

ለብ አለ ግ ሞቅ፣ ለሰስ አለ።

ለብ አለው በመጠኑ ሰከረ፣ ሞቅ አለው።

ለብ አደረገ ግ በመጠኑ አሞቀ።

ለብ አደረገው በመጠኑ አሰከረው።

ለብ ለብ ስ ሞቅ ሞቅ የተደረገ ወይም እሳት ያልገባው ክትፎ፣ ዱለት፣ ...።

ለተለተ ግ 1. ወዲያና ወዲህ አለ። 2. ተንከወከወ፣ ተንጠለጠለ፣ ዞረ፣ ተቅበዘበዘ።

ለትላታ (ለተለት) ቅ ከውካዋ።

ልትለታ ስ መወዝወዝ፣ መቅበዝበዝ፣ ወዲያና ወዲህ መባከን።

አለተለተ ግ ሰውነቱን አወዛወዘ።

ለተመ ግ 1. በሃይል መታ፣ ገጨ፣ ደቃ። 2. ወጋ (በግ)።

ተላተመ ግ ከአንድ ነገር ጋር ተጋጨ።

አላተመ ግ አጋጨ። *መኪናውን ከግንድ ጋር አላተመው።*

ለተተ ግ 1. ለፋ፣ ለሰለሰ። 2. ለዘዘ፣ ረሰበ።

ለት "እለት"ን ተመ.

-ለት (በየመደቡ ሲዘረዘር -ልኝ፣ -ልህ፣ -ልሽ፣ -ላት፣ ልን፣ -ላችሁ፣ -ላቸው፣ ይሆናል) በግስ መድረሻ ላይ እየተቀጠለ ለእሱ የሚለውን የድርጊት ተጠቃሚ የሚያሳይ ምእላድ። *ገንዘብ ላከለት /ደብዳቤ ፃፈላት።*

ለነቀጠ ግ የተገረደፈውንና በውሃ የራሰውን በቆሎ፣ ማሽላ፣... በእጅ ወፍጮ አልሞ ፈጨ፣ ደቆሰ።

ልንቅጥ ስ የተለነቀጠ እህል ሲጥ።

መለንቀጫ ስ ለመለንቀጥ የሚያገለግል የእጅ ወፍጮ።

ለንቋጣ ስ 1. በወይና ደጋና በቆላ የሚበቅል ልቡ ማሳጋ የሆነ አነስተኛ የእፅዋት አይነት። 2. (ዘ.ይ.) እቅመ ቢስ፣ ለዋሳ።

ለንባዳ (ለምባዳ) ቅ ኩልታፋ፣ ምላሰ ጎልዳፋ።

ለንቦጭ (ለምቦጭ) ስ ወፈርና ዘርበብ ያለ የታች ከንፈር።

ለንቦጩን ጣለ አኮረፈ።

ለንቦጫም ቅ (ስድብ) ለንቦጩ ትልቅ የሆነ።

ለንጨጭ ስ የጋማ ከብት ከንፈር።

ለንጨጫም ቅ (ስድብ) ትልቅ ወይም ከመጠን በላይ የወፈረ ከንፈር ያለው (ሰው)።

ለከለከ^{1} ግ 1. በምላሱ እየጨለፈ ጠጣ (ውሻ፣ ድመት፣...)። 2. ጠባ (ወተትን)። 3. በብዛት ጠጣ።

አለከለከ ግ በፀሃይ ሙቀት፣ በሩጫ፣ ...ምክንያት ከሚመጣ ድካም የተነሳ ቶሎ ቶሎ ተነፈሰ።

አስለከለከ ግ በማስሮጥ፣ በማራወጥ አደከመ፣ ቁና ቁና አስተነፈሰ።

ለከለከ^{2} "ሉ-ከሉ-ከ"ን ተመ.

*ለከሰከሰ

ልክስክሽ ስ ከብቶች ሲበሉ የሚያዝረከርኩት ገለባ፣ ሳር፣...።

ልክስክስ (ለከስካሳ) ቅ (ስድብ)1. ምናምንቴ፣ የማይረባ። 2. ለቃቃሚ፣ ልክፍክፍ። 3. አመንዝራ።

ተልከሰከሰ ግ 1.ቅጥ አጣ፣ ተዝረከረከ። 2. የማይረባ፣ ልክስክስ ሆነ። 3. በተወሰነ አካባቢ ብቻ መለስ ቀለስ አለ፣ ተመላለሰ። 4.ተድበሰበሰ፣ ተሸፋፈነ (ለነገር)። 5. (ዘይ.) አመነዘረ፣ ሸረሞጠ።

ተልከስካሽ [ሰይጣን] ስ በየቆሻሻው ላይ ይገኛል የሚባል ሰይጣን።

አልከሰከሰ ግ 1. ቅጥ አሳጣ፤ አዝረከረከ፤ በታተነ። 2. ጀምሮ፣ ነካ ነካ አድርጎ ተወ፣ (ምግብን፣ ስራን፣ ...)። 3. ልክስክስ አደረገ። 4. መሰስ ቀለስ እንዲል አደረገ። *እዚህ አካባቢ ምን ያልከሰክስሃል።*

ለከት^{1} ስ 1. ክዳን ወይም ግጣም። 2. መጠን፣ ወይም ገደብ። *ለአነጋገሩ ለከት የለውም።*

ለከት^{2} ስ ጥቢኛ፣ አነስተኛ ጸብ።

ለከከ "**ላከከ**" ን ተመ.

ለከፈ ግ 1. በመቅመስ፣ በመንካት፣ በመሳብ አረከሰ (ውሻ፣ ድመት፣ ...)። 2. ነካ፣ በሽታ አስተላለፈ (የታመመ ውሻ)። 3. ጀመረ፣ ያዘ (በሽታ)። *የዛሬ አመት የለከፈው በሽታ አሁንም አልለቀቀውም።* 4. ጀመር አድርጎ ተወ። *ምነው ለከፈህ ትተወዋለህ፣ ጨርሰህ ብላው እንጂ።* 5. ነገር ፈለገ፣ ተነኮሰ።

ለከፋ ስ ነገር ፍለጋ፣ ትንኮሳ።

ለካፊ ቅ ነገር ጫሪ፣ ተንኳሽ።

ልክፍት ስ 1. በርኩስ መንፈስ ምክንያት የሚመጣ በሽታ። 2. የበሽታ መነሾ። 3. የቆዳ በሽታ አይነት (ከፍቱን ባደረ ወይም ንፁህ ባልሆነ ውሃ በመታጠብ ይመጣል ተብሎ የሚታመን)።

ልክፍታም ቅ ወፈፌ።

ለካከፈ ግ 1. ቀመስ ቀመስ አድርጎ ተወ (ምግብን)። 2.ሁሉንም ለከፈ፣ ነካካ፣ አዳረሰ።

ልክፍክፍ (ለከፍካፋ) ቅ (ስድብ) ልክስክስ፣ የማይረባ፣ ለቃቃሚ።

ተለከፈ ግ በበሽታ ተያዘ፣ ታመመ።

በ______ተለከፈ 1. በ______ተያዘ፣ ተጠመደ። *በፍቅር ተለከፈ።* 2.በ_ ምክንያት በሽታ ያዘው፤ ለበሽታ ተጋለጠ። *በብርድ ተለክፎ ለሞት በቃ።*

ተለካከፈ ግ 1. ተጣላ፣ ተሰዳደበ። 2. ተነካካ።

ተላከፈ ግ 1.ተቃመሰ፣ ተካፈለ (ምግብን)። 2. ተጣላ፣ ተተናከሰ።

ተላካፊ ቅ ነገረኛ፣ ተሳዳቢ።

ተልከፈከፈ ግ ተልከሰከሰ፣ ልክስክስ ሆነ።

አለከፈ ግ አቀመሰ (ምግብን)።

አላከፈ ግ አቃመሰ፣ አዳረሰ (ምግብን)።

አልከፈከፈ ግ አልከሰከሰ።

*ለከፈ

ለካፋ(ልክፍ) ቅ ከሚጠላበት (ከማይፈለግበት) ቦታ የማይታጣ፣ ሳይጠሩት የሚመጣ፣ ልክስክስ፣ ቀላዋጭ።

ተለከፈ ግ ተጎተተ፣ ተደቀነ። *እፊቴ ላትለከፍ።*

ለካ^{1} ግ 1. ቁመትን፣ ስፋትን፣ ክብደትን፣ ... በተወሰነ መለኪያ መጠነ፣ ሰፈረ፣ መዘነ። 2. ልብስን፣ ጫማን፣ ... ልክ ይሆነው እንደሆን በመልበስ፣ በማድረግ ሞከረ።

ልክ ስ 1.መጠን፣ ብዛት። 2. ትክክል፣ እርግጥ፣ እውነት። 3. ሳይተርፍ ወይም ሳይጎድል በትክክል። *ልክ ሰባት ሰአት ላይ።* ቅ 4. ተስማሚ፣ ያልሰፋ፣ ያልጠበበ፣ ያላጠረ፣ ያልረዘመ (ልብስ፣ ጫማ፣ ...)።

ልኩን አገኘ 1. ተገቢውን ቅጣት አገኘ። 2. አቻውን አገኘ (ለጋብቻ)።

ልኩን የማያውቅ አቅሙን የማያውቅ፣ ያለ አቅሙ የሚንጠራራ።

ልክ ልኩን ነገረው ሙልጭ አድርጎ ሰደበው።

ልክ መጣ ተስማማ፣ ልክ ሆነ።

ልክና መልክ የለውም ቅጥ ያጣ ነው።

ልክ የለውም ብዙ፣ እያሌ ነው።

ልክ ገባ ተስተካከለ፣ ልክ ሆነ።

በልክ ሁን ስርአት ያዝ፣ ታረም፣ ተቆጠብ።

ከልክ ያለፈ ከመጠን በላይ የሆነ፣ በጣም ብዙ።

ያለ ልክ ከመጠን በላይ።

ልከኛ ቅ የተስተካከለ፣ ያላጠረ፣ ያልረዘመ፣ ያልቀጠነ፣ ያልወፈረ።

መለኪያ ስ ከቀንድ ወይም ከብርጭቆ፣... በትንሹ የተሰራ የአረቄ መጠጫ።

ተለካ ግ ልብስ ለማሰፋት ልኩን አሳወቀ።

ተለካካ ግ ተነፃፀረ፣ ተወዳደረ (ለምሳሌ ቁመት፣...)።

አለካካ ግ መጠንን፣ ክብደትን፣ ስፋትን አነፃፀረ፣ አወዳደረ።

ለካ^{2} **(ለካስ፣ ለካን)** ቃ. አ. ያልጠበቁት ነገር ሆኖ ሲገኝ ' አሁን ገና አወቅሁ፣ እንዲህ ነበር ወይ' የሚል አድናቆትን፣ መገረምን፣... የሚገልፁበት ቃል።

ለኮ^{1} ስ ከልባብ ጋር የተያያዘ ወይም የተቋጠረ የፈረስና የበቅሎ መሳቢያ ጠፍር ወይም ገመድ።

ለኮ^{2} ስ ከመሬት ገና ብቅ ያለ ሳር፣ ጨሌ።

ለኮሰ ግ 1. እሳትን አቀጣጠለ፣ አያያዘ። 2. ተኮሰ፣ ፈጀ፣ አቃጠለ። 3. አበራ (ችቦን፣ ሻማን፣ ...)። 4. አያያዘ፣ አቀጣጠለ (የኤሌክትሪክ ምድጃን፣ ምጣድን፣...)። 5. (ዘይ.) ጀመረ፣ ጫረ (ጠብን)።

መለኮሻ ስ የእሳት ማያያዣ (ሳይተር፣

ከብሬት፣ ...)።

አለኳኮሰ ግ አላኮሰ።

አላኮሰ ግ አጣሳ፤ አፋጀ፤ በነገር አጋጨ።

አላኳሽ ቅ ነገር እየቆሰቆሰ የሚያጣላ።

*ለኮሰ

ለኳሳ (ልኩስ) ቅ ለዋሳ፤ አቅመቢስ፤ ደካማ።

ልኩስ አለ ግ ውሽቅ፤ ውትፍ አለ። *ሰው ቤት ምን ወስዶ ልኩስ ላደረገህ።*

ልኩስኩስ (ለኮስኳሳ) ቅ 1. የማይረባ፤ ውትፍትፍ። 2. ንፅህናውን የማይጠብቅ፤ ፅዳት የሌለው፤ እርምጥምጥ።

ልኩስኩስ አለ ግ ተልኮሰኮሰ።

ልኩስኩስ አደረገ ግ አልኮሰኮሰ።

ተለኮሰ ግ ተወሸቀ፥ ተወተፈ።

ተልኮሰኮሰ ግ 1. ተርመጠመጠ፤ ተበላሸ፤ ቆሸሸ። 2. ተድበሰበሰ።

አልኮሰኮሰ ግ 1. አርመጠመጠ፤ አበላሸ፤ አቆሸሸ። 2. አድበሰበሰ።

ለኮፈ ግ በትንሹ መታ፤ ነካ አደረገ።

ልኩፍኩፍ (ለኮፍኳፋ) ቅ 1.በደንብ ያልተሰራ፤ ውሽልሽል። 2. ቁራት ያለው ስራ የማይሰራ።

ተልኮፈኮፈ ግ 1.ነካ ነካ ተደርጎ ተተወ፥ በደንብ ሳይሰራ ቀረ። 2. ተልጎመጎመ፤ ተጉተመተመ፤ በግልፅ ሳይናገር ቀረ።

አልኮፈኮፈ ግ 1. የማያረካ ስራ ሰራ፥ ነካ ነካ አድርጎ ተወ። 2. አልጎመጎመ፥ አጉተመተመ።

*ለወለወ

ለውላዋ (ለውለውቱ) ቅ ከውካዋ፥ ጠልጧላ፥ ዘዋሪ።

ለውለው አለ ግ ወዲያ ወዲህ አለ፥ ተንከወከወ።

ለወሰ ግ 1. እንደ ዱቄት ያለን ነገር ፈሳሽነት ካለው ነገር ጋር ቀላቅሎ አቦካ፤ አሸ። 2. በጭቃ፥ በእበት፥ ... አበላሸ፥ አቆሸሸ። *ልብሱን በጭቃ ለውሶ መጣ።* 3. በእግሩ ረጋገጠ፤ አጳከረ (ያደገ እህልን፤ ሳርን)። 4. አጥመለመለ፤ አደቀቀ፥ አዳከመ፥ ሃይል አሳጣ (በሽታ)። 5. መሬት ላይ ጥሎ መታ፥ ረገጠ።

ለዋሳ ቅ አቅመ ቢስ፤ ደካማ።

ልውስ ቅ 1. ለዋሳ። 2. በመፍራሙ የተቦካ ሊጥ።

ተለወሰ ግ 1.ተበላሸ፥ ተለቀለቀ፤ ተጨማለቀ (በቆሻሻ፥ በጭቃ)። 2. በበሽታ ምክንያት ተዳከመ፤ አቅም አጣ፥ ተጥመለመለ።

ተለዋወሰ ግ 1. ተበለሻሸ፥ ተጨመላለቀ (በቆሻሻ ነገር)። 2. ተልፈሰፈሰ፤ ዛለ፤ ደከመ፤ አቅም አጣ።

ለወጠ ግ 1. የአንድን ነገር ቀድሞ የነበረ ሁኔታ፥ ባህርይ፥ መልክ፥... በሌላ እንዲቀየር፤ እንዲተካ አደረገ። 2. አንድ ነገር ቀድሞ የነበረውን ሁኔታ፤ ባህርይ፤ መልክ፤... በሌላ ቀየረ። *ከመቆየቱ የተነሳ ቀለሙ ለወጠ።* 3. አንድን ነገር ሰጥቶ በምትኩ ሌላ ነገር ወሰደ። *እስክሪብቶውን በእርሳስ ለወጠ።* 4. ቀየረ፥ በሌላ ተካ። *አሮጌውን ልብስ ለውጦ አዲሱን ለበሰ።* 5. ቀየረ፥ ተበላሸ (የምግብ ጣእም፤ ሽታ)። 6. ቀድሞ ከነበረው አሻሻለ። *የኢኮኖሚ ፖሊሲው የህዝቡን ኑሮ ለውጦታል።* 7. የነበረበትን ቦታ ትቶ ወደ ሌላ ቦታ ሄደ። *ሰፈር ለወጠ።*

___ን በ___ ለወጠ ከ___ ይልቅ ___ን መረጠ፥ አስበለጠ። *ጓደኛውን በገንዘብ ለወጠ።*

ለውጥ ስ 1. አንድን ነገር የመስጠትና በምትኩ ሌላ የመውሰድ ሂደት ወይም ድርጊት። *በነፃ የተሰጠኝ ሳይሆን በለውጥ ያገኘሁት ነው።* 2. አንድን ነገር በመስጠት በምትኩ የተወሰደ ነገር። *ይህ መፅሃፍ የዚያኛው ለውጥ ነው።* 3. አዲስ ሁኔታ፤ የተለየ ነገር፤ ልዩነት። *ቀደም ሲል ከነበረው አሰራር ያሁኑ ብዙ ለውጥ ይታይበታል/በዚህና በዚያኛው መካከል ምንም አይነት ለውጥ የለም።* 4. የአንድ ህብረተሰብ የፖለቲካ ስርአት ወይም የመንግስት መዋቅር በሌላ መተካት።

ልዋጭ ስ 1. አንድን ነገር በመስጠት በምትኩ የሚወሰድ ትያሪ፥ ምትክ። ቅ 2. መቀየሪያ የሚሆን። *ልዋጭ ሸሚዝ የለውም።*

መለወጫ ስ መቀየሪያ።

ለዋወጠ ግ ቀያየረ።

መለዋወጫ ስ ላለቀ ወይም ለተበላሸ እቃ መተኪያ እንዲሆን የተቀመጠ እቃ።

ልውውጥ ስ አንድን ነገር የመስጠትና በምትኩ ሌላ የመውሰድ ድርጊት።

ልውጥ አለ ግ ቅይር አለ። *እሷ ላለመናገሯን ሲያይ ፊቱ ልውጥ አለ።*

ልውጥውጥ አለ ግ ተለዋወጠ።

ተለወጠ ግ 1. በፊት በነበረው ፋንታ ተተካ። 2. የነበረው ሁኔታ ተቀየረ። *የወጡ ቃና ተለውጧል/የገራቱ ሁኔታ እንደድሮው አይደለም፥ ተለውጧል።*

ተለዋጭ ቅ ተቀያሪ።

ተለዋጭ ቀጠሮ ስ ቀደም ሲል በተያዘው ቀን ቀጠሮ ፋንታ የተያዘ ሌላ የቀጠሮ ቀን።

ተለዋወጠ ግ 1.ተቀያየረ። 2. በንዴት ወይም በድንጋጤ መልኩ ወይም ፊቱ፥ ሁኔታው ከበፊቱ የተለየ ሆነ።

ተለዋዋጭ ቅ 1. አንድ ጊዜ አንዱን ሌላ ጊዜ ሌላውን የሚሆን፥ ቶሎ-ቶሎ የሚቀያየር። 2.

ወረተኛቱ ጠባዩ እንደየሁኔታው የሚቀያየር:: 3. ተወራራሽ:: *"ጀንበር" ወይም "ገንበር" በሚለው ቃል ውስጥ 'ጀ' ና 'ገ' ተለዋዋጭ ድምፆች ናቸው::*

አለዋወጠ ግ አንዱን ባንዱ ወይም አንዱን ወዳንዱ አቀያየረ፡ አዘዋወረ::

ማለዋወጫ ስ መቀያየሪያ::

አሳወጠ ግ 1.ቀየረ፡ ለወጠ:: *ባለቤት የወደደው አህያ ፈረስ ያሳውጣል::* 2. የአንዱን ወደ ሌላ አዛወረ፡ ቀያየረ::

አስለወጠ ግ አስቀየረ፡ ሌላ አስደረገ:: *የመኪናውን ጎማ አስለወጠ::*

ለዋ ግ ጅው አድርጎ ጠባ::

ለውዝ ስ እንደ ድንች በመሬት ውስጥ የሚያፈራና እየተቆላ የሚበላ ፍሬ፡ ኦቾሎኒ::

ለውጥ "ለወጠ" ስር ተመ::

ለዘለዘ ግ ጠባ፡ መጠመጠ::

ለዘበ ግ 1. ለሰለሰ፡ ሻካራነቱን ተወ:: 2. ለፋ(ለቆዳ):: 3. ገራም ሆነ::

ለዘብ ስ በበአል ቀን በቅኔ ማህሌትና በአደት ጊዜ (ታቦት ሲነግስ) ከፅናፅልና ከከበሮ ድምፅ ጋር በመጎዳኘት እየተመላለሰ የሚባል የወረብ ዜማ፡ ወረብ::

ለዘቡ ተባለ ግ ተወረበ::

ለዘብተኛ ቅ 1. ስህተት ሲፈፀም እያየ በቻልታ፡ በይሉኝታ፡ በግዴለሽነት የሚያልፍ:: 2. ወግ አጥባቂ፡ አክራሪ ያልሆነ:: 3. በአንድ የፖለቲካ ፓርቲ ውስጥ የፓርቲውን ደንብና ስርአት የማያከብርና የማያስከብር ፡ ቸልተኛ::

ለዘብተኝነት ስ ለዘብተኛ የሆነ የፖለቲካ አቋም::

ለዘብታ ስ እርጋታ፡ ቀስታ::

ልዝብ ቅ 1. ልስልስ:: 2 ገራም::

ልዝብ ሰይጣን ስ ሲያዩት ደግ፡ ገራገር፡ የዋህ የሚመስል ግብሩ ግን ሰይጣናዊ፡ ተንኮለኛ የሆነ ሰው::

ተለዘበ ግ ተወረበ፡ ለዘቡ ተባለ::

አለዘበ ግ 1. አለሰለሰ:: 2. አለፋ(ቆዳን):: 3. አገረመ፡ ገራ፡ አለሰለሰ (ጠባይን):: 4.ወረበ:: 5. በደንብ መላልሶ አጠና (ቅኔን፡ ዜማን)::

ለዘዘ ግ 1. ደረቅ የነበረው እንደ መርጠብ ወይም እንደ መራስ አለ፡ ለተተ:: 2. ተሰለቸ፡ ቸከ፡ ተጠላ::

ለዛዛ ቅ 1. እርጥበት ያለው ወይም በደንብ ያልደረቀ:: 2. ሞዛዛ፡ ቸካካ::

ተላዘዘ ግ 1. ለዛዛ ሆነ:: 2. ተሟዘዘ::

አለዛዘ ግ መጠነኛ እርጥበት እንዲኖረው አደረገ፡ አራሰ::

ለዛ ስ ውበት፡ ማማር፡ ማራኪነት (የአነጋገር፡ የመልክ፡...)::

ለዛ መጥጫ ቅ ለዛ የሌለው፡ ሲናገር የማያምርበት፡ ቸከ::

ለዛ ቢስ ቅ ውበት፡ ማራኪነት የሌለው (የአነጋገር፡ የመልክ፡ ...)::

ለየ ግ 1.መረጠ፡ ነጠለ፡ ከፈለ፡ ለብቻ አደረገ:: 2. ከለለ፡ ጋረደ:: *መኝታ ቤቱን በመጋረጃ ለየ::* 3. ጎደለ::*ከልጅ ልጅ ቢለዩ ላመትም አይቆዩ::* 4. አራቀ፡ አገለለ:: *የሚጠቅም ነገር ሲኖር ሁልጊዜ እሱን ይለዩታል::* 5. አስታወሰ፡ አወቀ::*ከሩቅ አገር የመጣውን ወንድሙን መጀመሪያ ሲያየው መለየት አቃተው::* 6. ታወቀ፡ ግልፅ ሆነ ወይም አሳወቀ፡ ግልፅ አደረገ:: *አቋሙ ለየ /አቋሙን ለየ::*

ለየለት 1. ቁርጡ ታወቀ፡ ተረጋገጠ:: 2. ጨርሶ አበደ::

አይለየን (ምር.) አሁን አብረን እንዳለን አብሮ ያቆየን::

የለየለት ቀና፡ ቀንደኛ:: *የለየለት ሌባ ነው::*

ይለይለት 1. ቁርጡ ይታወቅ:: 2. የመጣው ይምጣ፡ የሆነው ይሁን::

ይለይልን ይቀጣልን፡ አሸናፊው ይታወቅ::

ልዩ ቅ 1. ከሌላ ወይም ከሌሎች ጋር የማይመሳሰል፡ የተለየ:: *ከወንድሞቹ መሃል የሱ መልክ ልዩ ነው::* 2. ከተለመደው፡ ከመደበኛው የተለየ፡ ብልጫ ያለው:: *ለፈፀሙት ጀብዱ ልዩ ሽልማት ተሰጣቸው::*

ልዩ ልዩ ቅ የተለያዩ::

ልዩ ቅናሽ ስ በአንድ ምክንያት ለተወሰነ ጊዜ በእቃዎች ላይ የሚደረግ የዋጋ ቅናሽ::

ልዩ ፀሃፊ ስ አንድ ከፍተኛ ባለስልጣን የሚመለከታቸውን ጉዳዮች የሚመዘግብና የሚያስፈፅም የፅህፈት ቤቱንም ስራ የሚያከናውን ፀሃፊ::

ልዩነት ስ 1.አንዱ ከሌላው የሚለይበት ሁኔታ፡ አለመመሳሰል:: 2.አለመስማማት፡ አለመግባባት:: 3. በሁለት ነገሮች መካከል የሚታይ የመጠን ብልጫ ወይም ጉድለት::

መለዮ ስ 1. የወታደር ቆብ:: 2. አንዱ ከሌላው ተለይቶ የሚታወቅበት፡ መለያ::

መለዮ ለባሽ ስ መደበኛ ወታደር::

ለያየ ግ 1. ነጣጠለ፡ ለየብቻ አደረገ:: 2. አላቀቀ፡ ገላገለ:: 3. ከፋፈለ:: 4. አቃቃረ፡ አቆራረጠ::

ተለየ ግ 1. ተነጠለ፡ ብቻውን ሆነ፡ ተገለለ:: 2. ተከፈለ፡ ተከለለ:: 3. ታወቀ፡ ተማራ፡ ግልፅ ሆነ:: 4. ከሌሎች ልዩ ሆነ፡ ሌሎችን አልመሰለ

አለ።

በተለይ ተው.ግ. 1.በይበልጥ፥ ከሌሎች ይልቅ። *ከልጆቹ መሃል በተለይ እሷን ይወዳል።* 2. ከሌላው የበለጠ። *የሷ ቆንጆና በተለይ ነው።* 3. ለብቻ። *የሱ ድርሻ በተለይ ይቀመጥለት።*

የተለየ ቅ 1.ከሌላው የማይመሳሰል። *የተለየ ሃሳብ ካለ ማቅረብ ይቻላል።* 2. ከሌላው የባሰ፥ የበለጠ። *የዛሬው ብርድ የተለየ ነው።*

መለያ ስ ከሌላው ተለይቶ የሚታወቅበት ምልክት።

መለያ ቁጥር ስ አንድ ነገር መሰሉ ከሆነው ከሌላው ነገር ተለይቶ የሚታወቅበት ቁጥር።

ተለያየ ግ 1. ተነጣጠለ። 2. ተራራቀ(በሃሳብ፥ በቦታ፥...)። 3. ተፋታ (ከትዳር ጓደኛ)። 4.ተላቀቀ።

በተለያየ መንገድ በተለያየ አቅጣጫ፥ አንፃር፥ አኳያ።

መለያያ ስ 1. የአካል አንጓ፥ መጋጠሚያ። 2. መሰነባበቻ። *የመለያያ ግብዣ ተደርጎ ነበር።* 3. መገንጠያ (ለመንገድ)።

አለያየ ግ 1. ለየብቻ አደረገ፥ ለያየ። 2. አላቀቀ፥ ገላገለ። 3. አቆራረጠ፥ አቃቃረ። 4. አፋታ(ከትዳር)።

ለይስሙላ "ሰማ¹" ስር ተመ።

ለደለደ ግ ቀጭን የነበረው ፈሳሽ ወፈረ፥ ተምለገለገ (ተልባ፥ አብሽ፥ ...)።

ልድልድ ቅ የለደለደ፥ የወፈረ።

አለደለደ ግ 1. ለደለደ። 2.አወፈረ (ፈሳሽ ነገርን)።

ለደሰ ግ ለጠፈ፥ ቀባ።

ለደፈ ግ 1. አላግባብ ተፋ፥ ለጠፈ (ምራቅን)። 2. ተገቢ ባልሆነ መንገድ ለጠፈ፥ ቀባ (ጭቃን፥ ቆሻሻን፥...)። 3.የሚያስቀይም ወይም የሚያስከፋ ነገር ተናገረ።

ልድፍ ቅ አፉ እንዳመጣለት ተገቢ ያልሆነ ነገር የሚናገር።

ተለደፈ ግ ተለጠፈ፥ ተላከከ።

ለገለገ ግ ጠባ፥ መጠመጠ፥ መገመገ።

ለገመ ግ 1.አለመጠ፥ ጠመመ። 2. አቈመ (ቁስል)።

ልግም ስ ክፋት፥ ጥመት።

ልግመኛ ቅ አልምጥ።

ለገሰ ግ ቸረ፥ ሰጠ፥ ናኘ።

ለጋስ ቅ ቸር።

ለጋሽ ቅ 1. ቸር። 2. ሰጪ፤ ችሮታ አድራጊ

ልግስና ስ ችሮታ።

ተለገሰ ግ 1.ችሮታ አገኘ፥ ተቀበለ። 2. ችሮታ ተገኘ፥ ተሰጠ።

ለገበ ግ የተቀደደ ልብስን ጣፈ።

ለገተ ግ 1.ደቀነ። 2. ዘጋ፡ ወተፈ፥ ደፈነ።

ለገቻ ስ ፉክክር፥ ውድድር።

***ለገዘገዘ**

ልግዝግዝ (ለገዝጋዛ) ቅ ገትጋች፥ ነገር የማይቆርጥ።

ልግዝግዝ አለ ግ ተልገዘገዘ።

ተልገዘገዘ ግ ተንገታገተ፥ ነገር በቶሎ የማይቆርጥ ሆነ።

አልገዘገዘ ግ አንገታገተ፥ ነገር በቶሎ አልቆርጥ አለ።

ለገደ ግ 1. ወተፈ፥ ደፈነ፥ መረገ። 2. ዘጋ፥ ገደበ፤ ጋረደ፡ አገደ፥ ከለለ።

***ለገደ**

ለግድ ስ ለግጥ፥ ፌዝ።

ለግደኛ ቅ አላጋጭ፥ አሿፊ።

ተላገደ ግ አሾፈ፥ አላገጠ፥ ተዘባበተ።

***ለገገ**

ልጋግ ስ ከአፍ ውስጥ እየተሳበና እየተዝረበረበ የሚወጣ ለሃጭ።

ልጋጋም ቅ (ስድብ) 1. ለሃጫም። 2. (ዘይ.፥ስድብ) ከስታራነት፥ ቆፍጣናነት የሌለው።

ተላገገ ግ ተለፋደደ።

አለገገ ግ ለሃጩን አዝረበረበ።

***ለገጠ**

ለግጥ ስ ፌዝ፡ ቀልድ፡ ቧልት።

ለግጠኛ ቅ ፌዘኛ፡ ቀልደኛ፥ ቧልተኛ።

ልግጫ ስ ፌዝ፡ ቀልድ፥ ቧልት።

ተላገጠ ግ ተቃለለ፥ ተሞኘ።

አላገጠ ግ 1.አፌዘ፡ ቀለደ፡ አሾፈ። 2. አሞኘ፥ አቃለለ።

አላጋጭ ቅ አሿፊ፥ የሚያፌዝ።

ለገጥ ስ የከብት የታችኛው መንጋጋ።

ለገጣም ቅ ግንጭላም፥ አገጩ የረዘመ።

ለጋ ቅ 1. ቀንበጥ፥ ለምለም። 2. ያልበሰለ፥ ጮርቃ። 3.(ዘይ.) ልጅ እግር፡ ወጣት።

ለጋ ቅቤ ስ ያልቆየና ያልበሰለ ወይም ያልኮመጠጠ ቅቤ።

ለጋ ደመና ስ ቀለል ያለ አዲስ ደመና።

ለጋ ጎበዝ ስ ልጅ እግር፥ ወጣት፡ ሰታ።

ለጋ ጨረቃ ስ አዲሷ ሙሉ በሙሉ የማይታይ ገና አዲስ የወጣች ጨረቃ።

ለጋ¹ ግ 1.ሩርን ወይም ጥንግን በእጅ ወርወር

አድርጎ መሬት ሳታርፍ በዱላ መታ፤ ቀላ። 2. ኳሷን በረዥሙ መታ (የእግር ኳስ)። 3. መታ። *በዱላ ሊጋው።* 4. ገፋ፤ ገፈተረ። *ከቆምኩበት ለገቶኝ ሄደ።*

ተላጋ ግ ተጋጨ፤ ተላተመ።

አላጋ ግ አጋጨ፤ አላተመ።

ሊጋ² ግ ዥው አድርጎ ጠጣ።

ለግላጋ ቅ ቁመቱ ዘለግ ያለ ወጣት።

ለጎመ ግ 1. በበቅሎ ወይም በፈረስ አፍ ውስጥ ልጓም አስገባ። 2. እንዳይበላ የከብትን አፍ በገመድ ወይም በጠፍር አሰረ፤ ሸበበ። 3. ጥይት አጎረሰ (ጠመንጃን፣ ሽጉጥን)። 4. ስፌትን (አገልግል፣ ቁና፣ መሶብ፣...) በቆዳ ለበደ፤ ለበጠ፤ ሸፈነ፤ ከፈፈ። 5. እንዳይናገር አፉን በጨርቅ ጠቀጠቀ።

ልጉም [አፍ] ቅ መናገር ሲገባው የማይናገር፣ ሃሳቡን የማይገልፅ፣ ዝምታ የሚያበዛ።

ልጉም አለ ግ ዝም አለ፤ አልናገር አለ።

ልጓም ስ የከርቻ በቅሎና ፈረስ በጉዞ ላይ እያሉ እንዳይበሉና እንዳይጠጡ የሚከላከል፣ ፍጥነታቸውንና አቅጣጫቸውን ለመቆጣጠር የሚያስችል በአፋቸው ውስጥ የሚጠለቅ ዛብ ያለው ብረት።

ልጓም ለቀቀ 1. ፈረሱ የቻለውን ያህል እንዲጋልብ በልጓም መቆጣጠሩን ተወ። 2. (ዘይ.) ያለገደብ፣ እንደልቡ ሆነ።

ልጓም አላላ ቁጥጥሩን ቀነሰ።

ልጓም ጣለ በልጓም አልገታ አለ።

ልጉምጉም ቅ ፈታ አድርጎ የማይናገር።

ተለጎመ ግ 1. ስፌት (መሶብ፣ አገልግል፣...) በቆዳ ተለበደ። 2.(ጠመንጃ፣ ሽጉጥ) ጥይት ጎረሰ። 3. አልናገር አለ፣ ዝም አለ። 4. የመናገር ነፃነት አጣ፤ እንዳይናገር ተከለከለ።

ተልጎመጎመ ግ ፈታ አድርጎ አልናገር አለ።

አለጎመ ግ 1. ዝም አሰ፤ አልናገር አለ። 2-. አላመጠ።

አልጉም ቅ 1. ሃሳቡን ግልፅ አድርጎ አፍታቶ የማይናገር። 2. አልምጥ።

አልጎመጎመ ግ 1. መናገር የፈለገውን ነገር ግልፅ ወይም ፈታ አድርጎ አልናገር አለ፤ 2.አጉተመተመ።

ለጎደ ግ 1. ለጠፈ፤ ለደፈ (ጭቃን፣ ምራቅን፣ ንፍጥን)። 2. ላከከ (ጥፋትን)።

ተለጎደ ግ ተለጠፈ፤ ተለደፈ።

ለጎጠ ግ 1. ጎላ አድርጎ ወተፈ፤ አገባ። 2.ጎረሰ፤ አፉ ውስጥ አደረገ (ጡትን፣ ጣትን)።

ልጓጥ ስ ቢጋማ ከብት አፍ ላይ የሚደረግ የእንጨት ልጓም።

ለጠለጠ ግ 1. የቅባት እህልን ቅባት እስኪወጣው ድረስ ወቀጠ። 2. እስኪልም ድረስ ወቅጦ ጠፈጠፈ (ለምሳሌ ትንባሆን)። 3. ደጋግሞ በሃይል መታ፤ ደበደበ።

ልጥልጥ ቅ 1. እስኪልም ድረስ ተወቅጦ የተጠፈጠፈ (ትግ፣ ሰሊጥ፣...)። 2.የኖራ፣ የሰም፣...ጥፍጥፍ። 3. (ዘይ.) ወዘናው የሚያምር፣ ወዛም፤ በሚገባ የተቀለበ፤ የተመቸው።

ተለጠለጠ ግ 1. ወፈረ፤ አማረበት። 2. በብዛት ተከማቸ፤ ተገጠገጠ፤ ተተከለ (ህዝብ፣ ቤት፣ ድንኳን)።

አለጠለጠ ግ ወፈረ፤ ተመቸው።

ለጠሰ ግ አስተኛ፤ አጋደመ (ፀጉርን፤ ሰብልን፣ ...)።

ተለጠሰ ግ ተኛ፤ ተጋደመ (ፀጉር፣ ሰብል፣ ...)።

ለጠቀ ግ 1. ቀጠለ፤ ተከተለ። 2. (ዘይ.) ለስቃ፤ ልክክ አለ።

ልጥቅ አለ ግ 1 ተለጠቀ፤ ተጣበቀ።2- (ዘይ.) ተስማምቶ፤ ልክክ ብሎ ኖረ።

ተለጠቀ ግ 1.ተላከከ፤ ተጣበቀ።

ተለጣጠቀ ግ 1.ተጣበቀ፤ ተያያዘ። 2. ተከታተለ።

ተላጠቀ ዝ.ክ.

አለጣጠቀ ግ አጣበቀ፤ አያያዘ።

አላጠቀ ዝ.ክ.

ለጠበ ግ በለጠብ ከደነ።

ለጠብ(ልጣብ) ስ መክደኛ።

ለጠጠ¹ ግ ሳበ፤ ወጠረ።

ልጥጥ ቅ ጅንን፤ ኩሩ።

ተለጠጠ ግ 1. ተሳበ፤ ተጎተተ (ለምሳሌ ላስቲክ)። 2. ኮራ፤ ተጀነነ።

ለጠጠ² ግ 1. ከመኑ የተረፈውን ድር ቀንሶ አወጣ። 2. ሳጠ፤ ቀረፈ።

ልጣጭ ስ 1. ተቀርፎ ወይም ተልጦ የሚነሳ የብርቱካን፣ የሎሚ፣ የሙዝ፣...ልባስ ወይም ሽፋን። 2. መጎ ከሚችለው በላይ በመሆኑ ተቀንሶ የቀረ ትርፍ ድር።

ለጠጠ³ ግ መታ።

ለጠጦ ስ ረዘም ብሎ ቀጠን ያለ በትር።

ለጠፈ ግ 1.በግድግዳ፣ በስሌዳ፣...ላይ አጣበቀ (ስእልን፣ ወረቀትን፣...)። 2. መረገ። 3. ለደፈ (ምራቅን፣ ንፍጥን፣...)። 4. አመካኘ፤ አላከከ። *የራሱን ጥፋት በእኔ ላይ ለጠፈ።*

ለጣፊ ቅ 1. ነገር ለቃቃሚ፤ አሾክሿኪ። 2. ራሱን የማይችል፣ ጥግ ፈላጊ፣ በሰው የሚመካ።

ልጥፍ ስ ገና ያልተለሰነ የጭቃ ቤት ምርግ።

ልጥፍ አለ ግ ተጠጋ፥ ጥብቅ አለ።

ተለጠፈ ግ 1. ተላከከ፥ ተጣበቀ። 2. ተጠጋ፥ በጣም ቀረበ። *ግድግዳ ላይ ተለጥፎ ያዳምጥ ነበር።*

ተለጣፊ ቅ ራሱን ችሎ ሳይሆን ሌላውን ተጠግቶ የቆመ፥ የተሰራ። *ተለጣፊ ቤት /ተለጣፊ ሱቅ።*

ለጥ

ለጥ አለ ግ 1. ተጋደመ፣ ለሽ አለ። 2. ለረዥም ሰአት ተኛ፥ እንቅልፍ ወሰደው። 3. እንዲፈፅም የሚጠበቅበትን ተግባር ሳያከናውን ዝም ብሎ ቆየ።

ለጥ ብሎ እጅ ነሳ በጣም አጎንብሶ ሰላምታ ሰጠ።

ለጥ ያለ ሜዳ አባጣ ጎርባጣ የሌለው፥ ወለል ያለ ሜዳ።

ለጥ ሰጥ አለ 1. ያለምንም ተቃውሞ አሜን ብሎ ተገዛ። 2. ስርአት ያዘ።

ለጥ ሰጥ አደረገ 1. ያለምንም ተቃውሞ አሜን ብሎ እንዲገዛ አደረገ። 2. ስነ ስርአት እንዲከበር አደረገ።

ለፈለፈ ግ 1. ብዙ ተናገረ፥ አወራ፣ ቀባጠረ። 2. ደጋግሞ አነሳ፥ ወተወተ። *እኔማ አይሆንም ብዬ ለፍልፌ ነበር፥ የሚሰማኝ አጣሁ እንጂ።*

ለፍላፊ ቅ (ስድብ) ቀባጣሪ፣ ማውራት የማይሰለቸው።

ተለፋለፈ ግ 1. በመዉዉህ ተነጋገረ። 2. ተጨቃጨቀ፥ ተነታረከ (በመዉዉህ)።

አለፋለፈ ግ አነታረከ፣ አጨቃጨቀ።

አስለፈለፈ ግ 1. እንዲናገር፥ ምስጢር እንዲያወጣ አደረገ። 2. አናገረ። *ላይበመኝ ምን አስለፈለፈኝ።*

***ለፈሰፈሰ**

ልፍስፍስ (ለፈስፋሳ) ቅ 1. አቅመቢስ፣ ደካማ። 2. ሃሞተ ቢስ።

ልፍስፍስ አለ ግ ተልፈሰፈሰ።

ልፍስፍስ አደረገ ግ አልፈሰፈሰ።

ተልፈሰፈሰ ግ 1. ደከመ፣ አቅም አጣ። 2. ሃሞተ ቢስ ሆነ፥ ወኔ አጣ።

አልፈሰፈሰ ግ 1. አዳከመ፣ አቅም አሳጣ። 2. ሃሞተ ቢስ ወይም ወኔ ቢስ አደረገ።

ለፈተተ ግ ለዘዘ።

ልፍትት (ለፍታታ) ቅ ለዛዛ።

ለፈደደ ግ በእርጥበት ምክንያት በቀላሉ አልታረስ፥ አልወጋ አለ (መሬት)።

ለፈዳም (ለፈዲያም) ቅ (ስድብ) ዘላዛባ፥ አነጋገሩ የማይጥም።

ለፍዳዳ (ለፈደድ) ቅ (ስድብ) 1. ሲናገር ቃላት የሚነትት፥ አቀላጥፎ የማይናገር (የህፃናትን ንግግር አይጨምርም)። 2. ጨምላቃ። 3. ነዝናዛ፥ ጨቅጫቃ።

ተለፋደደ ግ የማይጥም ነገር ተናገረ፥ ተጨማለቀ።

ለፈጠቀ ግ ጨቀየ፥ ተጨማለቀ፥፥

ለፍጫቃ ቅ 1. ጨምላቃ። 2. ለፍዳዳ። 3. ነዝናዛ፥ ጨቅጫቃ።

ልፍጭቅ አለ ግ ጭምልቅ አለ።

ተለፋጠቀ ግ 1. ተጨማለቀ። 2. ተለፋደደ። 3. ተነዛነዘ፥ ተጨቃጨቀ።

አለፋጠቀ ግ 1. አጨማለቀ። 2- ሲበላ አፉን አጮሀ።

ለፈፈ ግ ሰው እንዲሰማ ጮሆ ተናገረ፥ አወጀ።

ተለፈፈ ግ ታወጀ፥ ተነገረ።

ለፋ ግ 1. ደከመ፥ ጣረ፣ ጋረ፥ ኳተነ፥ ማሰነ። 2. ታሽቶ ወይም ተረግጦ ለሰለሰ፣ ለዘበ፣ ለተተ (ቆዳ)። 3. ለረዥም ጊዜ ከማገልገሉ የተነሳ ተጎዳ፣ አረጀ።

ለፍቶ መና 1. ጥሮ ግሮ የማያልፍለት፥ የማይሳካለት። 2. የልፋት፥ የድካም ዋጋ የማይገኝበት።

ለፍቶ አዳሪ ስ ጥሮ ግሮ፥ በሚያገኘው የሚኖር፣ ሰርቶ አዳሪ።

ልፊያ ስ 1. የቀልድ ትግል ወይም ድብድብ።

ልፋት ስ 1.ድካም፥ ጥረት፥ ግረት። 2. ውጤት የሌለው ፍሬቢስ ድካም።

ልፍ ቅ የተለፋ (ቆዳ)።

ተለፋ ግ ለፋ፥ ለሰለሰ፥ ለዘበ (ቆዳ)።

ተላፋ ግ የቀልድ ታገለ ወይም ተደባደበ።

አለፋ ግ 1. አደከመ፥ አኳተነ፥ አማሰነ። 2. አለሰለሰ፥ አለዘበ (ለምሳሌ ቆዳን)። 3. ብዙ ጊዜ ተገለገለበት (ልብስን፥ ጫማን፥...)።

አልፊ ቅ አድካሚ።

አስለፋ ግ አደከመ።

ለፎ ስ ፈረሰኛ ያልሆነ የጥንት እግረኛ ወታደር።

ሉ የ"ለ" ፈደል ካእብ ዘር።

ሉህ (ሉኽ) ስ 1. ያልተቆረጠበት ሌጣ ወረቀት፥ ብራና። 2 . የተላገ ወይም የለዘበ ሳንቃ፥ ሰሌዳ።

ሉል ስ 1. ብልጭልጭና ለስላሳ የሆነ ከባህር የሚገኝ የከበረ ድንጋይ፣ የእንቁ አይነት። 2. ንጉስ

ሉል 3ኛ ፍቺ

በሚነግስ ጊዜ በእጁ የሚይዘው ክብ ሆኖ የተሰራ የአለም ተምሳሌት። 3. በኳስ ቅርፅ የተሰራ የአለም ካርታ።

ሉቃሳም (ልቋሳም) ቅ (ስድብ) 1. ቅጋራም 2. ደካማ፣ ልፍስፍስ።

ሉባ ቅ ቀልጣፋ፣ ንቁ፣ ጎበዝ።

ሉባንጃ (ልባንጃ) ስ ጥሩ ሽታ ያለው የእጣን አይነት።

ሉተራን ስ ከፕሮቴስታንት ሃይማኖት አንዱ የሆነውና በማርቲን ሉተር ስም የተሰየመው ሃይማኖት ወይም የሃይማኖቱ ተከታይ።

ሉአላዊ ቅ ነፃ የሆነ፣ ምሉእ ስልጣን ያለው (ሃገር፣ መንግሥት)።

ሉአላዊነት ስ ምሉእ የሆነ መብት፣ ነፃነትና የስልጣን የበላይነት።

ሉካንዳ (ልኳንዳ) ስ የስጋ መሸጫ ቤት።

ሉክ ስ የ"ሉህ"ን 1ኛ ፍቺ ተመ.

ሉጢ ቅ (ስድብ) 1. አንድ ቦታ ረግቶ የማይቀመጥ፣ ከሁካዋ። 2. ነገር አመላላሽ።

ሉጫ (ላሁጫ) ስ ከርዳዳ ያልሆነ፣ ለስላሳ ፀጉር።

ሊ የ"ለ" ፊደል ሳልስ ዘር

ሊ __ "ል-"ን ተመ.

ሊሉ ስ 1. የአሞራ አይነት። 2. ከወረቀት ወይም ከስስ ጨርቅ የሚሰራና ከጫፉ ላይ በረዥም ክር አስረው በመያዝ ወደ ሰማይ ሲለቁት የሚንሳፈፍ የልጆች መጫወቻ።

ሊሬ ስ የጣሊያን ገንዘብ ስም።

ሊስት ስ የሰው፣ የእቃ፣...ስም ዝርዝር ወይም ዝርዝሩ የተፃፈበት ወረቀት።

ሊስትሮ ስ 1. ጫማ ጠራጊ። 2. ጫማ ጠራጊ ቀለምና ቡርሽ የሚያስቀምጥበትና ጫማ አስጠራጊውም እግሩን የሚያሳርፍበት ትንሽ ሳጥን።

ሊሻን "ኒሻን"ን ተመ.

ሊሾ ስ በአሸዋና በሲሚንቶ በልሙጡ የተለቀለቀ ወለል ወይም ግድግዳ።

ሊቅ (ብ.ቁ.**ሊቃውንት**) ስ 1. በትምህርት የበሰለ፣ የተራቀቀ፣ ምሁር፣ አዋቂ። 2. እንደ ሃይማኖተ አበው፣ አፈወርቅ፣ ቄርሎስ፣ ኤጲፋንዮስ፣ ቅዱስ፣ አቡሻህር የመሳሰሉ ሃይማኖት ነክ መፃህፍት የሚጠሩበት ስም።

ከሊቅ እስከ ደቂቅ ከትልቅ እስከ ትንሽ፣ ከልጅ እስከ አዋቂ፣ ሁሉም ሰው።

ሊቀ ሊቃውንት ቅ ከሊቃውንት በላይ የላቀ እውቀት ያለው።

ሊቀ መላእክት ቅ የመላእክት አለቃ የሆነ።

ሊቀመንበር ስ 1. የአንድ ኮሚቴ፣ ማህበር፣ ቦርድ፣...መሪ። 2. የአንድ ጉባኤ ወይም ስብሰባ መሪ።

ሊቀመኳስ ስ እንደ ንጉስ የሚለብስና በንጉስ አጠገብ የሚቆም የንጉስ ባለሟል።

ሊቀ አርድእት ስ በቤተ ክህነት ትምህርት ቤት የተማሪዎች አለቃ።

ሊቀ ካህናት ስ የካህናት አለቃ።

ሊቀ ዲያቆን (ሊቀ ዲያቆናት) ስ የዲያቆናት አለቃ።

ሊቀ ጉባኤ ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) የጉባኤ፣ የስብሰባ መሪ፣ አለቃ።

ሊቀ ጠበብት ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) በቤተ ክርስቲያን ከአለቃ በታች ያለ ማእረግ።

ሊቀ ጳጳሳት (ብ.ቁ.**ሊቃነ ጳጳሳት**) ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ማእረጉ ከጳጳሳት በላይ ከፓትርያርክ በታች የሆነ መንፈሳዊ አባት።

ሊባ ስ በሰሜንና በምእራብ መካከል ያለ የአለም ማእዘን አቅጣጫ።(በተጨማሪ ማእዘን ስር ተመ)።

ሊብሬ ስ የመኪና ባለቤትነት መታወቂያ ደብተር።

ሊትር ስ 1. አንድ ኪሎ ግራም የሚሆን ውሃ የሚይዘውን ያህል ቦታ ሊይዝ የሚችል ፈሳሽ። 2.ከላይ የተጠቀሰው የፈሳሽ መጠን መለኪያ።

ሊትሮ ስ አንድ ሊትር ፈሳሽ ሊይዝ የሚችል ጠርሙስ።

ሊቼንሳ ስ የንግድ ወይም የመንጃ ፈቃድ።

ሊጋባ ስ ወደ ቤተ መንግስት የሚገቡና ከቤተ መንግስት የሚወጡ ሰዎችን እንዲቆጣጠር ይሾም የነበረ የእጋፋሪዎችና የከልካዮች አለቃ መጠሪያ።

ሊጥ ስ 1.በውሃ የራሰና የተለወሰ ዱቄት፣ ቡኮ። 2. በደንብ ያልበሰለ (ለምሳሌ ዳቦ)።

ሊጡ ተነሳ ኩፍ አለ፣ ቦካ።

ሊጦን ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) በቤተክርስቲያን ቄሶች በየእለቱ ተራ አስገብተው የሚያዜሙትና የሚደግሙት የምስጋና ፀሎት።

ሊፍት ስ ዘመናዊ በሆኑና ብዙ ፎቅ ባላቸው ህንፃዎች ላይ ሰዎች ለመውጣትና ለመውረድ/ የሚገለገሉበት በኤሌክትሪክ የሚሰራ መሳሪያ፣ አሳንሱር።

ሊፕስቲክ ስ ሴቶች ከንፈራቸውን የሚቀቡት ቀለም።

ላ የ "ለ" ፊደል ራብእ ዘር።

ላ – "ል-"ን ተመ.

ላሁጫ "ሉጫ"ን ተመ.

ላህይ ስ 1. ውበት፥ ደምግባት፡ ወዘና። 2. የድምፅ ቃና።

ላሊበላ ስ 1. ሳይነጋ በሌሊት በየሰው ቤት እየዞረ ወይም ተዝካርና በርግ ባለበት እየሄደ በዜማና በግጥም የሚለምን፤ ሃሚና፤ ኣባንንዳ፤ ኣባውዲ፤ ደብራሆም። 2. (ዘይ፥ስድብ) ለፍላፊ፥ ምላሰኛ።

ላላ ግ 1. የታሰረው ወይም ጠብቆ የነበረው እንደመርገብ፡ እንደመፈታት ኣለ። 2. ቀጠን ኣለ (ሊጥ)። 3. ከመብሰል ወይም ከመበስበስ የተነሳ ሉክሉክ፥ ትምክ ትምክ ኣለ። 4. ደከመ፥ ዛለ፥ ሃይልና ጥንካሬ ኣጣ። 5. ለቀቅ፥ ቀለል ኣለ (ቁጥጥር፥ ህግ፥ እስር፥...)።

ላላቴ ስ ለስላሳ የሆነ ትንሽ ዳቦ፥ ሀብስት።

ልል ቅ 1. ያልጠበቀ፥ የረገበ። 2. በኣካል ወይም በባህርይ ጠንካራ ያልሆነ።

ኣላላ ግ 1. ጠብቆ የነበረውን ወይም፥ የተወጠረውን ለቀቅ ኣደረገ፤ ኣረገበ። 2. ቁጥጥሩን ኣቀለለ፥ ለቀቅ ኣደረገ።

ላመ ግ 1.የተፈጨው ወይም የተወቀጠው ወይም የተደቆሰው፥... በጣም ደቀቀ። 2. ለረዥም ጊዜ ከመለበሱ የተነሳ ሳሳ፥ ብን ኣለ።

ልም ቅ 1.የላመ፥ የደቀቀ። 2. ልስልስ። 3.ጥንካሬ የሌለው (ሰውነት)።

ኣላመ ግ በመውቀጥ ወይም በመፍጨት ወይም በመሰለቅ፥...በጣም ኣደቀቀ።

ላመል "**ኣመል**" ስር "**ለኣመል**"ን ተመ.

***ላመጠ**

ልማጭ ስ ታኝኮ የተተፋ የኣገዳ ምጣጭ፥ እኛኪ፥ ብሳቶ።

ኣላመጠ ግ 1. የጎረሰውን (ምግብ) ኣኘከ። 2. እንደመቆርጠም እያደረገ ኣመመ። 3. (ዘይ.) ሰውን በክፉ ኣነሳ፤ ኣማ።

ላመ ፊጅ ስ ብዙ ሰው መያዝ የሚችል ትልቅ ድስት፥ ሰታቴ፤ መካከለኛ ጎሳ።

ላሚዳ "**ላይዳ**"ን ተመ.

ላም ስ 1. መውለድ የጀመረች የቀንድ ከብት።(ስእሉን የቤት እንስሳ ስር ተመ.)። 2. (ዘይ.) ገር፥ የዋህ። 3.(ስድብ) ሞኝ።

ላም ኣለኝ በሰማይ የማይገኝ ነገር፤ በሩቅ፥ በምኞት ብቻ ያለ።

የላም ልጅ ስ ወተት፥ እርጎ፥ ኣይብ።

የላም ጨው ስ 1.ላም በምትታለብበት ጊዜ ሳታስቸግር ወተት እንድትሰጥ የሚያልሷት ኣሞሌ ጨው፤ መላሽ። 2. ሲበሉት ጨው ጨው የሚል በፍሬው ላይ እሾህ ያለበት ቀላ ያለ የእፅዋት ኣይነት።

ላም ላጊ ስ መጠኑ ከድመት ኣነስ የሚልና ላም የሚጠባ ኣጡሬ።

ላም እንገት ፈሪ።

ላምባ ስ ለኩራዝ የሚያገለግል ነዳጅ፡ ጋዝ ፡ ናፍታ።

ላምባዲና ስ የእጅ ባትሪ።

ላምዛን ስ ኣነባበር።

ላምፋ (ላንፋ) ስ 1. የመቃ፥ የኣገዳ፤ የበቆሎ፡...ቅጠል። 2. (ዘይ.፥ ስድብ) እቅመቢስ፡ ደካማ።

ላሰ ግ 1. በምላሱ ጠረገ፥ ኣበሰ። 2. የሚበላን ወይም የሚጠጣን ነገር በምላሱ ወሰደ፤ ተመገበ። *ድመቷ ወተቱን ላሰችው።* 3. ጥርግ ኣደረገ፥ እሟጠጠ፥ ጨረሰ (ስራን፥ መብልን፥...)። 4. ፈጀ፤ ኣቃጠለ፡ ለመጠጠ (እሳት)። 5. ሰረቀ፥ መነተፈ። *ገንዘቤን ከኪሴ ላሰኝ።*

መላሽ ስ 1. ከብት የሚልሰው ኣሞሌ ጨው። 2. ጉቦ ወይም መማለጃ።

ምላስ ስ 1.ለመናገር፥ ለመብላት፡ ለመቅመስ፤ ለመላስ የሚያገለግል በኣፍ ውስጥ የሚገኝ የሰውነት ክፍል።(ስእሉን ኣፍ ስር ተመ.)። 2. በቅርፁ፥ በእንቅስቃሴው፥... ምላስን የሚመስል ነገር (ለምሳሌ የሚዛን ክብደት ጠቋሚ፥ የእሳት ነበልባል)። 3. (ዘይ.) ልፍለፋ። *ሰውየው ምላስ ያበዛል።*

ምላሱ ጥቁር ነው የተናገረው መጥፎ ትንቢት ወይም እርግማን ይደርሳል።

ምላሱን ኣስረዘመ ለነገር ቸኮለ፥ ቀደም ቀደም ኣለ፡ ኣፉን ኣሞጠሞጠ፥ ብዙ ተናገረ።

ምላሱን ኣውለበለበ ብዙ ለፈለፈ፥ተናገረ።

ምላስ ለቀቀበት ልፍለፋ ኣበዛ።

ምላስ ዱልዱም ቅ ኣንደበቱ ፈታ ብሎ ቶሎ ቶሎ መናገር የማይችል።

ምላሰኛ (ምላሳም) ቅ 1.ለፍላፊ፥ ተናጋሪ፥ ቀባጣሪ። 2. ነገረኛ።

ምላስና ሰንበር ስ ከላም ወይም ከበሬ ምላስና ሰንበር የሚዘጋጅ ምግብ።

ተላላሰ ግ 1. የፍቅር፥ የመዋደድ መሳሳም ተሳሳመ። 2. በነነ፥ ተባነነ (ዱቄት) 3. (ዘይ.) ከልብ ያልመነጨ ምስጋና እርስ በርስ ተመሰጋገነ፥ ተወዳደሰ።

ኣላሰ ግ 1. ኣሞሌ ጨውን ለከብት መገበ። 2. በጥፊ ኣጮለ፥ ኣጠናፈረ። 3. ጠጅ ወይም ጠላ ውስጥ ማርን፥ ቅራሪ ወይም ጠላ ውስጥ ድፍድፍን ጨመረ። 4. (ዘይ.) ትንሽ ገንዘብ ሰጠ። *ከትርፉ ትንሽ ኣላሰኛል።*

ማላሻ ስ በበሰለ ወይም በቀጠነ ጠጅ ወይም ጠላ ውስጥ የሚጨመር ማር ወይም ድፍድፍ።

ላሰሰ ግ ኣረምን፥ እህልን፥ ሳርን፥...በብዛት

ጨርሶ ነቀለ።

ልሳሽ ስ በአንድ ክረምት አንድ ማሳ ላይ ተዘርቶ የነበረው ሰብል እንደ ታጨደ ብሩን እየነቀሉ ወዲያው የሚዘሩት የጓያ ወይም የሽምብራ ዘር።

ላስቲክ ስ 1. ሲስቡት የሚለጠጥና ሲለቁት የቀድሞ ቅርፁን የሚይዝ ጎማነት ያለው ነገር። 2. እንደ ጨርቅ በስሱ የተዘጋጀና ለጠረጴዛ ልብስነት፥ ለእቃ መያዣ፥... የሚያገለግል ፕላስቲክ። 3. የተለያዩ ነገሮችን (ብር፥ የተጠቀለለ ነገር፥...) አስሮ ለመያዝ የሚያገለግል ቅርፁ ክብ የሆነ ተለጣጭ ቀጭን ጎማ።

ላስቲክ ጫማ ስ ከጎማ ወይም ፕላስቲክነት ካለው ነገር የሚሰራ ጫማ።

ላሸ ግ 1. አልይዝ አለ፤ ላላ፤ ሟለጠ። 2. ተኮላተፈ፤ ተሳሰረ (አንደበት)።

ላሸቀ ግ 1. ከመተሻሸት፥ ከመፈጋፈግ የተነሳ ለፋ፤ ለሰለሰ (ቆዳ)። 2. ላላ፥ ጥብቀት አጣ። 3. ሟለጠ ለምሳሌ ወናፍ፥...። 4.በሰበሰ፥ ተጨማለቀ። 5. ከነበረው ደረጃ ወረደ፥ ዝቅ አለ (በአስተሳሰብ፥ በችሎታ)።

ላሽ ስ ፀጉርን የሚመልጥ በሽታ።

ላቀ ግ ከፍ አለ፥ በለጠ።

ላቂያ ስ ብልጫ።

ይልቅ(ይልቅስ፥ይልቁንስ፥ ይልቁንም) ተው.ግ. በይበልጥ። *ትምህርቱን ከማቋረጥ ይልቅ ቢቀጥል ይሻለዋል/በቃል ከተነገረ ይልቅ በፅሁፍ የሰፈረ ነዋሪነት አለው/ እሱ ችኩል ነው ይልቅስ እሷ አስተዋይ ነች።/ ይልቁንስ እሱ ቢመጣ ጥሩ ነበር / ችግሩ አልተቃለለም ይልቁንም እየተባባሰ ሄደ።*

ላቅ ያለ(የላቀ) ቅ 1.ከፍ ያለ። *ላቅ ያለ ገንዘብ አገኘ።* 2. የሞቀ፥ የደመቀ።*ላቅ ያለ አቀባበል ተደረገላቸው።*

አላቀ ግ 1. ከፍ አደረገ። 2. አስበለጠ። *ከኔ ለሱን አልቃ ወደ እሱ ሄደች።*

ላቆጠ ግ 1. በካ፤ ተለወሰ። 2. ተጨማለቀ፤ ጨቀየ።

ልቁጥ ቅ የተለወሰ፥ የተበካ።

ልቁጥ በርበሬ ስ ተፈጭቶ በውሃ የታሸ ወይም የተለወሰ በርበሬ፤ ድልህ።

አላቆጠ ግ 1. ለወሰ፥ አበካ። 2. አጨማለቀ።

*ላበ

ላብ (ላበት) ስ ከመሮጥ፥ ብዙ ከመስራት፥ ከሙቀት፥ ከህመም፥... የተነሳ ከሰውነት ቆዳ ውስጥ የሚወጣ ፈሳሽ።

ላብ ላብ አለው የፍርሃት፥ የጭንቀት ስሜት ተሰማው።

ላብ አጠመቀው ከድንጋጤ፥ ከድካም፥... የተነሳ በጣም አላበው።

ላብ አደር ስ የምርት መገልገያ መሳሪያዎች ባለቤት ያልሆነ፥ ለህልውናውም ሲል የስራ ሃይሉን ለካፒታሊስቱ በመሸጥ በዘመናዊ ፋብሪካዎችና ኢንዱስትሪዎች ውስጥ ተቀጥሮ በሚያገኘው ምንዳ የሚተዳደር ሰራተኛ፤ ወዛደር።

ላቦት(ላበት) ስ ከፈሳሽ ወይም እርጥበት ካለው ነገር ላይ በሙቀት ምክንያት የሚነሳ ተን፥ እንፋሎት።

አላበ ግ 1. ከሙቀት፥ ከድንጋጤ፥...የተነሳ ከሰውነት ላብ ወጣ። 2. ከድንጋጤ፥ ከጭንቀት የተነሳ የፍርሃት ስሜት ተሰማ፤ ፍርሃት ፍርሃት አለ።

ላባ^{1} ስ በዶሮ፥ በአሞራ፥ በወፍ፥...ቆዳ ላይ የሚበቅል እንደ ፀጉር ያለ የአካል ሽፋን።

ላባ

ላባ ቀረሽ ቅ ጨርሶ ሊያብድ ትንሽ የቀረው (ሰው)።

ላባ ኳስ ስ (ስፖ.) ክብ በሆነ ቡሽ ላይ የተሰካኩ ላባዎች ያሉት የባድሚንተን መጫወቻ።

ላባ ኳስ

ላባ^{2} ስ ጠላትን ወይም ሌባን ለመከላከል በግንብ ወይም በካብ አጥር ላይ የሚተከል ሹል እንጨት ወይም ብረት ወይም የጠርሙስ ስባሪ።

ላቦራቶሪ ስ 1.ደም፥ ሽንት፥ አይነምድር፥ ... የሚመረመርበት ክፍል ወይም ሙከራዎች የሚካሄዱበት ስፍራ፤ ቤተ ሙከራ።

ላቦት "*ላበ" ስር ተመ.

ላተነ ግ እየተሟሰሰ ተዋሃደ፤ ተነነፈ።

አላተነ ግ እያሟሰሰ አዋሃደ፤ አነነፈ።

ላት^{1} ስ 1. በተፈጥሮው ስብ የሆነ የበግ ጅራት 2. የካራ ወይም የጎራዴ እጀታ።

ላት^{2} ስ ጥራጥሬን ለመያዝ ወይም ለመለካት የሚያስችል ከመዳፍ በላይ ያለ መሃል እጅ።

ላንድ ላት ዓቂላ።

-ላት "-ለት"ን ተመ.

-ላቸው ዝ.ክ.

-ላችሁ ዝ.ክ.

ላንሲታ(ላንሴታ) ስ የክብደትን ልክ ወይም መጠን የሚያሳይ የሚዛን ምላስ፤ ሙልብልቢት።(ስእሉን ሚዛን ስር ተመ.)።

ላንቁሶ ስ 1. ልጡ ሲላጥ ዝልግልግና ማላጋ የሆነ፤ እየተሸነሸነም ለአጥርና ለግድግዳ መማገሪያ የሚያገለግል ረዥምና ወፍራም ሃረግ። 2. ሃይልና ጥንካሬ የሌለው፣ አቅመቢስ ሰው።

ላንቃ ስ በመሃል ምላስ ትይዩ ያለው የአፍ ውስጥ የላይኛው ክፍል፤ ጣሪያ።(ስእሉን አፍ ስር ተመ.)።

ላንቃ ካባ "ካባ ላንቃ"ን ተመ.

ላንፋ "ላምፋ"ን ተመ.

ላእላይ

ላእላይ መዋቅር ስ በማርክሳዊ ሌኒናዊ ፍልስፍና አመለካከት መሰረት፣ በህብረተሰብ ውስጥ በሚገኙ የኢኮኖሚ ግንኙነቶች ላይ ተመስርተው፣ የህብረተሰቡን የፖለቲካ፤ የህግ፤ የሃይማኖት፣ የፍልስፍና፤... ንቃተ ሀሊና የሚያንፀባርቁ ሃሳቦች፤ ድርጅቶችና ተቋሞች።

ላከ ግ 1.እቃን፤ መልእክትን፣...በሰው ወይም በሌላ ነገር ሰደደ፤ አስተላለፈ፤ አቀበለ። 2. መልእክት እንዲያደርስለት ወይም ጉዳዩን እንዲሞላለት አንዱ ሰው ሌላውን ሰው እንዲሄድ አደረገ። 3. ሳያኝክ ወይም ሳያላምጥ ዋጠ።

ላኪ ስ 1.ሸቀጥን ለውጭ ገበያ የሚያቀርብ ነጋዴ ወይም ድርጅት። 2. የደብዳቤው ወይም የመልእክቱ ባለቤት። *በደብዳቤው ላይ የላኪው ስም አልተፃፈም።*

ልኡካን (ነጠ.ቁ.**ልኡክ**) በፊደል ተራው ተመ.

መልአክ በፊደል ተራው ተመ.

መልእክት (**መልክት፤ መላክት**) ስ በደብዳቤ፤ በቃል፤... ከአንድ ሰው ወደ ሌላ ሰው የሚላክ ነገር፤ ጉዳይ።

መልእክተኛ (**መላክተኛ**) ስ አንድን መልእክት ለማድረስ ወይም አንድን ጉዳይ ለማስፈፀም ወይም ለመፈፀም የሚላክ ሰው።

ተላከ ግ 1. መልእክት ለማድረስ፤ ጉዳይ ለመፈፀም ወይም ለማስፈፀም ታዞ ሄደ። 2. ተሰደደ፤ እንዲሄድ ተደረገ (መልእክት፣እቃ..)።

ተላከበት ግ መልእክት እንዲነገረው፤ እንዲደርሰው ተደረገ።

ተልእኮ በፊደል ተራው ተመ.

ተላላከ ግ1.ወደ ተለያዩ ቦታዎች እየተላከ መልእክት አደረሰ፤ የታዘዘውን ፈፀመ። 2. ደብዳቤ ተፃፃፈ፤ በደብዳቤ ወይም በሰው አማካይነት ሃሳብ ተለዋወጠ።

የመላላክ ትምህርት "**የተልእኮ ትምህርት**"ን ተመ.

ተላላኪ ስ በመስሪያ ቤት ውስጥ መልእክት የማድረስን፤ የመላላክን ስራ የሚሰራ ሰራተኛ።

ላከከ (ለከከ) ግ 1. ቀባ፤ ለጠፈ። 2. አጣበቀ። 3. በሌላ አመካኘ፤ አሳበበ (ጥፋትን)። 4. አጋባ፤ አስተላለፈ. (በሽታን)።

ልክክ አለ ግ 1. ልክ መጣ፤ በትክክል ገጠመ። 2. ተጣጋ፣ ተጣበቀ። 3. ተስማማ፤ ለመደ፤ አብሮ ኖረ።

ልክክ አደረገ ግ በደንብ አድርጎ፤ በሚገባ ተመገበ። *ምሳውን ልክክ አደረገ።*

ተላከከ ግ 1. ተጣበቀ፣ አልለቅ አለ። 2. ተመካኘ፤ ተሳበበ። 3. ተጣጋ፣ አልለይ አለ።

አላከከ ግ አመካኘ፤ አሳበበ።

***ላወሰ**

ላወስ አለ ግ ተላወሰ።

ተላወሰ ግ 1. ተንቀሳቀሰ፣ ተነቃነቀ። 2. ወዲያ ወዲህ አለ፤ ሄደ።

አላወሰ ግ አንቀሳቀሰ፤ አነቃነቀ።

አያላውስም 1.አያንቀሳቅስም፤ አያነቃንቅም። 2. ጊዜ፤ ፋታ አይሰጥም።

ላውንድሪ ስ የልብስ ንፅህና መስጫ ድርጅት ወይም መስሪያ።

ላዙና ስ በአንዳንድ የቀንድ ከብቶች የሃሞት ከረጢት ውስጥ የሚገኝ ወርቃማ መልክ ያለው ጠጠር።

ላዛ ቅ ለስላሳ፣ ለሙጤ (ፀጉር)።

ላዛኛ ስ ጠፍጣፋ ከሆነ ፓስታ የሚዘጋጅ የምግብ አይነት።

ላይ መዋ. 1. ከአካባቢው ከፍታማ የሆነ ቦታ። *የስራ አስኪያጁ ቢሮ የሚገኘው ላይ ነው።* 2. የአንድ ነገር ውጫዊ አካል፤ ገፅታ፤ ክፍል። *የውስጡን እንጃ እንጂ ላዩስ ጥሩ ነው።* 3. የአንድ ነገር አካል አናታዊ ገፅታ፣ ክፍል።*መፅሃፉ ጠረጴዛው ላይ ተቀምጧል።* 4. በአንድ አካል ላይ ወይም ውስጥ መጣበቅን፤ መለጠፍን፤ መታሰርን፤ መገኘትን፣... የሚያመለክት። *ግድግዳው ላይ ያለው ስእል /ልብሱ ላይ ቆሻሻ አለ/* እጁ ላይ ያለው ሰአት */ወረቀት ላይ ፃፈ/* ፊቱ ላይ ብጉር መጣበት */አውቶቡስ ላይ ተሳፈረ።* 5. አንድ ነገር የሚካሄድበት ጊዜ ወይም ሰአት። *ሰርጉ ላይ ተገኝቷል/ስብሰባ ላይ አልነበረም /ስራ ላይ ቀልድ የለም/ በመሄድ ላይ ነው።* 6. የተወሰነ ቦታን፤ ጊዜን የሚጠቁም። *መንገድ ላይ*

ይጫወታሉ/ሁለት ሰዓት ላይ እመጣለሁ/ በኋ ላይ ይዘንባል። 7. አንድን ነገር አስመልክቶ ለመናገር ወይም አቅጣጫን፣ አንፃርን፣ አኳያን ለመጠቆም የሚያገለግል። *ጠላት ላይ ዘመተ /እዚህ ላይ አንድ ችግር አለ/በእሱ ላይ እምነት አለኝ /በሠራው ላይ ሳቀበት/ በግቢ ላይ ግብር ተጣመረ /ትንባሆ ላይ ቀረጥ ተጣመረ።* 8. አንድ ነገር ከስንት ቦታ እንደተከፈለ የሚያሳይ። *ዳቦውን አራት ላይ ከፈለው።*

ላይ ላዩን 1. አፋፋ፣ አፋፋን፣ ጋራ ጋራውን። 2. ጠለቅ ሳይል፣ ነካ ነካ፣ ገረፍ ገረፍ፣ ውጪ ውጪውን። 3. ከአንገት በላይ፣ ለይምሰል። *ላይ ላዩን ይስቃል።*

ላይ ታች አለ 1.ሽቅብ ቁልቁል አለ፣ ወጣ ወረደ፣ ለፋ። 2.ዘባበደ።

ላይ ታች አለው ትውከትና ተቅማጥ አጣደፈው።

ላይና ታች ረገጠ 1. ተወሳገደ፣ መስመሩን ለቀቀ። 2. ዘባበደ፣ ቀበጠረ።

በላዩ ላይ በተደራቢ። *በላዩ ላይ ሌላ ወዳጅ ያዘች።*

በላይ በማስበለጥ። *ከሁሉም በላይ እሱን እወደዋለሁ።*

በላይ በላዩ ወዲያው ወዲያው፣ ያለማቋረጥ፣ በአናት በአናቱ። *በላይ በላዩ ወለደች/ ጠጁን በላይ በላዩ ሞላለት።*

ከላይ እስከ ታች ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ፣ ከትንሽ እስከ ትልቅ፣ በጠቅላላው፣ በሙሉ።

ከላይ እንደተመለከተው በፊት፣ ቀደም ብሎ እንደተመለከተው።

ከላይ ከላዩ 1. ከአፍ ከፉ፣ ላይደራረብ። 2. ዋና ዋናውን፣ ከአናት ከአናቱ ።

ከላይ የወረደ ከእግዚአብሔር የመጣ፣ የታዘዘ (ብዙውን ጊዜ ለክፉ ነገር)።

ወደ ላይ አለው አስታወከው፣ አስመለሰው።

የበላይ አለቃ፣ ሹም፣ ባለስልጣን።

የበላይ ባለስልጣን ዝ.ከ.

ላይ ቤት ስ 1. ገነት፣ መንግስተ ሰማያት። 2. (ቤ.ክህ.) በጎንደር የሚገኝ የአቋቋም፣ የትርጓሜ መፃህፍት ትምህርት ቤት ወይም የትምህርት ጉባኤ፣ በአቋቋም በዜማና በመፃህፍት አተረጓጎም ከታች ቤት የሚለይበት የራሱ የሆነ ስልትና ባህል ያለው የትምህርት ተቋም።

ላይኛው ቅ በላይ በኩል ያለው።

የላይኛው ጌታ ስ እግዚአብሔር።

ላይተር ስ ሲጋራ ለመለኮስ ወይም እሳት ለማያያዝ የሚያገለግል፣ ጋዝ እየተሞላ እሳት መፍጠር የሚችል መሣሪያ፣ መለኮሻ።

ላይዳ (ላሜዳ) ስ እንደ አካፋ ሆኖ ከእንጨት የተሰራና በውድማ ላይ በነፋስ አማካይነት ፍሬን ከእብቅና ከገለባ ለመለየት የሚያገለግል የግብርና መሳሪያ።

ላይዳ

ላይዳ አለ አውድማ ላይ የተወቃን እህል በላይዳ ወደ ላይ በመበተንና ለነፋስ በመስጠት ፍሬን ከገለባ ለየ።

ላዳን ስ ከሰንደዶ ወይም ከሸንበቆ፣... የሚሰራ የእህል መስፈሪያ፣ መለኪያ (መጠኑ እንደአካባቢው ይለያያል)።

ላገ[1] ግ ትክክል እንዲሆን፣ እንዲለሰልስ፣ እንዲለዝብ አድርጎ ፋቀ፣ ጠረበ (እንጨትን)።

መላጊያ ስ ለእንጨት መፋቂያ፣ ማስተካከያ የሚያገለግል በመካከሉ ስል ብረት (ምላጭ) ያለበት የአናጢዎች መሳሪያ።

መላጊያ

ላገ[2] ግ 1. ጠባ፣ መገመገ፣ መጠመጠ። 2. አለበ። 3. ራበ፣ ሞረሞረ። *ራብ ይዞ ይልገኛል።*

ላገ[3] ግ አማሰለ፣ አዋሃደ፣ አበማማ (ሰንገር)።

ላጊ ስ የጤፍን ፍሬ ከገለባው በልቶ አገዳውን ባዶ የሚያስቀር ተባይ።

ላጠ[1] ግ 1.የአንድን አካል ቆዳ፣ ሽፋን፣...አነሳ፣ መለጠ፣ ገፈፈ፣ ገሸለጠ። 2. ፈጀ፣ አቃጠለ፣ ለመለመ። 3. ገረፈ፣ መታ። 4. አሽሟጠጠ፣ ሸረደደ፣ አማ፣ ስም አጠፋ። *በነገር ላጠው።*

ልጣጭ ስ የሽንኩርት፣ የብርቱካን፣ የሎሚ፣...ቅርፊት ወይም ሽፋን።

ልጥ ስ በዛፍ፣ በተክል፣... ቅርፊት ውስጥ የሚገኝ የእንጨት ሽፋን።

ልጠ ስ የተፈተገ ሰንዴ እብቅ፣ ገለባ፣ አሰር።

ልጠ ጉርዱ ስ ከተፈተገ ሰንዴ የሚወጣ አሰርና እንቅጥቃጭ።

ልጠ ጉርዱ አወጣ ፈተገ፣ አነፈሰ፣ አበጠረ።

ተሳጠ ግ 1. ተመሰጠ፥ ተገፋፋ፥ ተቀረፈ። 2. ተገረፈ፤ ተመታ።

ተሳሳጠ ግ 1.ተገሸላለጠ፥ ተገማጠበ፤ በጣም ተሳጠ። 2. ፊት ለፊት ተሰዳደበ ወይም በአሽሙር ተሸራደደ።

መሳሳጫ ስ ከዶሮ ክንፍ በታች ከግራና ቀኝ የሚወጣ የስጋ ብልት።(ስእሉን የዶሮ ብልት ስር ተመ.)።

ሳጠ^2 ግ 1.በፍጥነት አወጣ፤ መዘዘ (ሽጉጥን፥ ጎራዴን፥ ገንዘብን፥...)። 2. ሰረቀ። *ሌባ ገንዘቡን ከኪሱ ሳጠው።*

ሳጥ ሳጥ አለ ግ ፈጠን ፈጠን ብሎ ሄደ፤ መንቀር መንቀር አለ።

ሳጥ አደረገ ግ 1.በፍጥነት አከናወነ፥ ፈፀመ። 2. ዘረጥ አደረገ (ፈስን)።

ሳጥ ሳጥ አደረገ ግ በፍጥነት አከናወነ (ስራን፥ ተግባርን፥...)።

ተሳጠ ግ 1.ፈረጠጠ፤ ሸሸ። 2. ሄደ፥ ነጎደ።

ሳጠ^3 ስ 1. ሻረ፥ ከስልጣን አወረደ። 2. ሻረ፤ ፍርድን ለወጠ።

ተሳጠ ግ ተሻረ፥ ተለወጠ፤ ቀረ። *ፍርዱ ተሳጠ።*

***ሳጠ**

ሳጤ ስ 1. ትዳር የሌለው፤ ብቸኛ ሰው። ቅ 2.እፍረተ ቢስ፥ ባለጌ።

ሳጤ መሳጤ ስ ሃብት፤ ንብረት ያላፈራና ቤተሰብ ያልመሰረተ ሰው።

ሳጥ ሳጥ አለ ግ ሰራ ፈታ፤ አውደለደለ።

ሳጨ ግ 1. ስለት ባለው ነገር (ለምሳሌ በምላጭ) ፀጉርን ከአካል ቆዳ ላይ ፍቆ፤ ፈግፍጎ አነሳ፤ መለጠ። 2. አታለለ፥ ሸነገለ።

ልጭ ቅ ፀጉሩን የተሳጨ።

ምሳጭ ስ 1. ፀጉርን ለመላጨት የሚያገለግል አነስተኛና ስለ የሆነ ስለታም ብረት። 2. ጠመንጃ፥ ሽጉጥ፥... ለመተኮስ የምትሳብ ቆልማማ ብረት። 3. (ዘይ.) በአነጋገሩ ቀልጣፋ የሆነ፥ ብልጣ ብልጥ።

ምሳጭ አፍ (አፈ ምሳጭ) ቅ አፈ ጮሌ፥ ብልጥ፥ ሰውን በንግግር ማታለል የሚችል።

ተሳጨ ግ ስለት ባለው ነገር ፀጉሩ ተነሳ፥ ልጭ ሆነ።

ሳጂስ ስ በእርሳስ ወይም በቀለም የተፃፈ ፅሁፍን ፥ንድፍን ከወረቀት ላይ ፈግፍጎ ለማጥፋት የሚረዳ ጎማነት ያለው የፅህፈት መሳሪያ።

ሳፈ ግ 1. አቃጠለ፥ ፈጀ፥ ሳጥ አደረገ። 2. መነተፈ፥ ሞጨለፈ፤ ነጠቀ። 3.በፍጥነት አከናወነ (ስራን፥ መብልን፥...)። 4.ቆረጠ። *ቢላዋ እጁን ሳፈው።* 5. ቅርፊትን ከልጥ ለየ፤ ላጠ፤ ቀረፈ። ሲ.መታ። *በጥፊ ሳፈው።*

ሳፍ ሳፍ አደረገ ግ በፍጥነት አከናወነ (ስራን፥ መብልን፥...)።

ተሳፈ ግ ተላጠ፥ ተገሸለጠ።

ሳፈፈ ግ ላጠ፤ ሞለፈፈ።

ልፋፊ ስ ተልጦ የተነሳ ቅርፊት፤ ግልፋፊ።

ሴ የ "ሰ" ፊደል ሃምስ ዘር።

-ሌለ ከሌላ ምእላድ ጋር እየተጣመረ የሚነገርና '-ሳልኖረ፤ አልተገኘ' የሚል ፍች የሚሰጥ መድረሻ ምእላድ። *ከሌለ፥ ስለሌለ፥ በሌለ፥ እንደሌለ፥...።*

ሌሊት(ሌት) ስ 1. ፀሃይ ከምትጠልቅበት ጊዜ ጀምሮ እስከምትወጣበት ድረስ ያለው ጊዜ። 2. ጠዋት፤ ማለዳ፤ ንጋት ላይ።

ሌት ተቀን ተው.ግ. ሌትና ቀን፤ ዘወትር፤ ያለማቋረጥ፤ ያለ እረፍት።

የሌሊት ልብስ ስ እንደ ብርድ ልብስ፤ አንሶላ፤ ፒጃማ፥...ያለ ሌሊት የሚለበስ ልብስ።

የሌሊት ወፍ ስ ሌሊት የምትበር እንደ ወፍ ክንፍ፤ እንደ አይጥ ጥርስና ጆሮ ያላት የምትታጠባ ወፍ።(ስእሉን ወፍ ስር ተመ.)።

የሌሊት ዘበኛ ስ ሌሊት ሌሊት የሚጠብቅ ዘበኛ።

ሌላ ቅ 1. ከበፊቱ የተለየ። *ይህ የቅድሙ አይደለም፥ ሌላ ነው።* 2. ሁለተኛ፥ ተጨማሪ። *ይህን ሳትጨርስ ሌላ አይገኝም።* 3.ከታወቀው፤ ከተለመደው፥ ከሚገመተው ሳይሆን ከተለየ። *ሴትዮዋ ከሌላ ወለደች።*

ሌላ ሌላ አለ ጣእሙ፤ ቃናው ቀየረ፤ ለወጠ።

ሌላ ነው ግሩም፤ ድንቅ ነው። *ለሷ የተገዛው ልብስ ሌላ ነው።*

ሌላ ጊዜ አሁን ሳይሆን በሌላ ሰአት፥ ወቅት።

ሌላው ቀርቶ ቢያንስ ቢያንስ፥ በትንሹ።

በሌላ መንገድ በሌላ ዘዴ፤ በተጨማሪ። *ሂሳቡን በሌላ መንገድ ቢሰራውም ውጤቱ ተመሳሳይ ነው/መፅሃፍ የማንበብ ልምድ ጊዜን ላልባሌ ቦታ ከማባከን ይቆጥባል፤ በሌላ መንገድ ደግሞ የእውቀት አድማስንም ያሰፋል።*

በሌላ በኩል ባንፃሩ። ደመወዝ ተጨምሯል፤ በሌላ በኩል ግን ኑሮ ተወዷል /በአንድ በኩል ይገነባል፤ በሌላ በኩል ይበላል።

በሌላ አባባል/አነጋገር/አገላለፅ ይህም ማለት። *ከተለያዩ ሰዎች ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት ማድረግ ለአደጋ ያጋልጣል፤* በሌላ አባባል አንድ ለአንድ መወሰን ይበጃል ማለት ነው።

የሌላ እንዳይመስል ከሚገመተው ወይም

ሊሆን ከሚገባው ውጪ እንዳይመስል።

ከ ___ ሌላ ከ ___ በተጨማሪ። *ከዚህ ሌላ ምን ትፈልጋለህ።*

ሌማት ስ ከአክርማ ወይም ከስንደዶ፣... የሚሰራና ለእንጀራ ማስቀመጫነት የሚያገለግል መሶብ።

ሌባ^{1} ስ 1. የሌላን ሰው ንብረት ሰርቆ የወሰደ ሰው። ቅ 2. የራሱ ያልሆነውን ነገር ሰርቆ የሚወስድ። 3. (ዘይ.) ውሸታም፣ አጭበርባሪ፣ አታላይ።

ሌባ ሚዛን ስ ትክክለኛ ያልሆነ ሚዛን፤ የአንድን ነገር የክብደት መጠን ያለአግባብ ከፍ ወይም ዝቅ አድርጎ እንዲያሳይ የተሰራ ሚዛን።

ሌባ ሻይ ስ ሌባን አድኖ ለመያዝ ይረዳል ተብሎ የሚታመንበትን መድሃኒት ከጠጣ በኋላ ወገቡን በመቀነት ተይዞ ሌባን የሚያድን የቀድሞ ጊዜ ሌባ አሳሽ።

ሌባ ውጋት ስ ድንገተኛ የሆነ የውጋት በሽታ፤ ህመም።

ሌባ ዝናም ስ ሳይታሰብ ድንገት መጥቶ ሰብል የሚያጠፋ ዝናም።

ሌባ ጣት ስ ከእጅ አውራ ጣት ቀጥሎ ያለው አመልካች ጣት።(ስእሉን እጅ ስር ተመ.)።

የሌባ ተቀባይ ስ ሌባ እየሰረቀ የሚያመጣውን የሚገዛ ወይም እየተቀበለ የሚያስቀምጥ ሰው።

ሌባ^{2} ስ በሚሰነጠቅ ወይም በሚፈለጥ እንጨት መካከል በመሆን አንደኛውን ሰንጣቂ ከሁለተኛው ጋር የሚያያይዝና እንዳይለያይም የሚያደርግ የእንጨት ስንጣሪ።

ሌባ ጎማ ስ ከሙጫ ቀልጦም ያለ፤ በተለይ የተሽከርካሪዎችን ጎማ ከቸርኪው ለመለየት የሚያገለግል ከብረት የተሰራ መሳሪያ።

ሌቢቻይ (ሌቢቻ) ስ በሚጫኑ የጋማ ከብቶች ጅራት ስር የሚገባ ጨርቅ ወይም ቆዳ የተጠመጠመበት የመጫኛው ክፍል፤ ውዴሳ።

ሌተና ኮሎኔል ስ በሻለቃና በኮሎ-ኔል መካከል ያለ የወታደር ማእረግ።

ሌተና ጀኔራል ስ ከሜጀር ጀኔራል በላይ ያለ የወታደር ከፍተኛ ማእረግ።

ሌት "ሌሊት"ን ተመ.

ሌችዋ ስ በተለይ በባሮና አኮቦ ወንዝ አካባቢ የሚገኝ፤ ረጅምና ከርዳዳ ፀጉር ያለው፣ መልኩ በጠቅላላ ጠቆር ያለ ቡናማ የሆነ ሳር በል እንስሳ። ሴቷ ሌችዋ ቀንድ የላትም።(ስእሉን የዱር እንስሳት ስር ተመ.)።

ሌንቦ ስ ለንቦጭ።

ሌዘ ሃረግ ስ እየተሰነጣጠቀ ለቤት መማገሪያ የሚያገለግል ቅጠሉ ሰፋፊ የሆነ ሃረግ።

ሌጣ ቅ 1. ነጠላ፣ ብቸኛ። *ለገሰ ሚስት የለውም፤ ሌጣ ነው።* 2. ምንም የሌለው፣ ምንም ያልያዘ፣ ባዶ። *አራስ ልትጠይቅ ሌጣ እጇን መጣች።* 3. የምታጠባው፣ የምታዝለው ወይም በሆዷ የተረገዘ ልጅ የሌላት (ሴት)። 4. ያልተጫነ (ፈረስ፣ በቅሎ፣...)።

ሌጣ ምድር ስ አትክልት፣ እፅዋት፣... ያልበቀሉበት ባዶ ወይም ገላጣ ስፍራ።

ሌጣ ሰማይ ስ ደመና፣ ጭጋግ ወይም ጉም የሌለበት የጠራ ሰማይ።

ሌጣ ሰው ስ ቤተሰብ የሌለው ብቸኛ ሰው።

ሌጣ ቀን ስ በአል የሌለበት የስራ ቀን።

ሌጣ ወረቀት ስ ያልተፃፈበት፣ ባዶ ወረቀት።

ሌጦ ስ ያልተለፋ የበግ ወይም የፍየል ቆዳ።

ል የ "**ለ**" ፊደል ሳድስ ዘር።

ል- መነ.(ከ"**ይ**" ከ "**እ**" ድምፆች በፊት ሲመጣ "ሊ-"፣ "ላ-" ይሆናል) ምኞትን፣ ምክንያትን ወይም ሌላ ድርጊትን በሚጠቁሙ ግሶች መነሻ እየገባ ግሱ እንዳያስር የሚያደርግ ምእላድ። *ልመጣ እፈልጋለሁ /ላየው ጓጉቻለሁ/ ሊሄድ ቸኩሏል።*

-ልህ "-ለት"ን ተመ.

ልል "ላላ"ስር ተመ.

ልመደው ስ የሁለት አሞሌ ጨው ያህል መጠን ያለው አንድ ትልቅ አሞሌ ጨው።

ልሙጥ "ለመጠ" ስር ተመ.

ልሟም "ለመመ" ስር ተመ.

ልም "ላመ" ስር ተመ.

ልምሻ(ልምሾ) ስ ሽባ የሚያደርግ በሽታ፤ ፖሊዮ።

ልምቡጥ "ልንቡጥ"ን ተመ.

ልም አይን ቅ አይኑ ደካማ የሆነ (ሰው)።

ልም እቃ ስ ምራን እንዲሁም የመርገጥና የማነቆ ጠፍር በጥቅሉ የሚጠሩበት ስም።

ልምጭ^{1} ስ ቅርፊቱ ጥቁር አረንጓዴ የሆነና ለጥርስ መፋቂያነት የሚጠቀሙበት የእፅዋት አይነት።

ልምጭ^{2} ስ "**ለመጠ**^{1}" ስር ተመ.

ልሳን ስ 1. አንደበት፣ የመነጋገሪያ ህዋስ። 2. ቋንቋ። 3. ዘቢያው የሚገባበት የዶማ ወይም የመጥረቢያ ጉሮሮ። 4. ማንኛውም የፖለቲካ፣ የሃይማኖት፣...ድርጅት አስተያየቱን፣ ፍላጎቱን፣ እምነቱን የሚገልፅበት ጋዜጣ፣ መፅሔት። 5. የሰይፍ ስለት።

ልሳኑ ተዘጋ መናገር አቃተው፣ ተሳነው።

ልሳነ ምድር ስ ሾጠጥ ብሎ ወደ ባህር የገባ

መረት።

ልሳን ባህር ስ ሾጠጥ ብሎ ወደ የብስ የገባ ባህር።

ልሳን ብዙ ቅ 1. ብዙ ወይም የተለያዩ ቋንቋዎችን የሚጠቀም። 2. ብዙ ወይም የተለያዩ ቋንቋዎችን የሚያተራጉም ወይም በብዙ ቋንቋዎች የተዘጋጀ (ለምሳሌ ልሳነ ብዙ መዝገበ ቃላት)።

ልሳን እሳት ስ የእሳት ነበልባል ጫፍ።

ልሳን ክልኤ ቅ 1. ሁለት ቋንቋ ብቻ የሚናገር። 2. ሁለት ቋንቋዎችን የሚያተራጉም ወይም በሁለት ቋንቋዎች የተዘጋጀ (ለምሳሌ ልሳነ ክልኤ መዝገበ ቃላት)።

ልሳን ዋህድ ቅ 1. አንድ ቋንቋ ብቻ የሚናገር። 2. ባንድ ቋንቋ ብቻ የተዘጋጀ (ለምሳሌ ልሳነ ዋህድ መዝገበ ቃላት)።

ልሻ ስ ለስላሳ የአረህ ወይም የገደል ሳር።

ልሻ ፀጉር ስ ለስላሳ፣ ሉጫ ፀጉር።

-ልሽ "-ለት"ን ተመ.

ልቃቂት "ለቀቀ" ስር ተመ.

ልቅ ዝ.ክ.

ልቅሞሽ "ለቀመ" ስር ተመ.

ልቅና "አለቃ" ስር "እልቅና"ን ተመ.

ልቆ ""*ለቃ" ስር ተመ.

ልቋሳም "ሉቃሳም"ን ተመ.

ልቡና "ልብ" ስር "ልቦና" ን ተመ.

ልባብ ስ ከጠፍር የተሰራ፣ ፈረስና በቅሎ ራስ ላይ የሚጠለቅ የፊት ላይ ጌጥ።

ልባንጃ "ሉባንጃ"ን ተመ.

ልብ ስ 1. በሰውነት ውስጥ የደምን ዝውውር የሚያከናውን ውስጡ ክፍት የሆነ የሰውነት ክፍል። 2. እንደ አእምሮ ሁሉ የስሜት፣ የሃሳብ፣... መፍለቂያ እንደሆነ ተደርጎ የሚወሰድ አካል። 3. የዳቦ ቡጥ ወይም የእንጨት፣ የፍሬ፣...መሃለኛው ክፍል። 4. ከአገናዛቢ ምእላዶች ጋር እየሆነ ሃሳብ፣ ስሜት፣... የሚል ፍቺ የሚሰጥ (ለምሳሌ ልቤ ተሸበረ/ልቡ ተጨነቀ)።5. (ዘይ.) ድፍረት፣ወኔ።



ልብ

ልቡ ሄደ በሃሳብ ተዋጠ፣ ሃሳቡ ወደሌላ ሄደ።

ልቡ መታ 1. የልቡ ምት ፍጥነት ጨመረ፣ ከተገቢው መጠን ወይም ሁኔታ ውጪ ሆነ። 2. ደነገጠ፣ ፍርሃት ተሰማው።

ልቡ ሞተ ደከመ፣ ሰነፈ፣ ወኔ አጣ።

ልቡ ረጋ ከሃሳብ፣ ከጭንቀት፣... ነፃ ሆነ።

ልቡ ራራ ርህራሄ ተሰማው፣ አዘነ።

ልቡ ራሰ ያሰበው ወይም የተመኘው ሆነለት፣ ተሳካለት፣ ደስ አለው፣ ረካ።

ልቡ ሰባ ትእቢት ያዘው፣ አልታዘዝ አለ።

ልቡ ሳሳ 1. በነገር ተሰላቸ። 2. በበሽታ፣ በመጠጥ፣... የተነሳ አቅም አነሰው።

ልቡ ሸፈተ ያሰበውን ነገር ለማድረግ ተነሳሳ፣ ሃሳቡ ወደ ሌላ ሄደ።

ልቡ ሻከረ "ሆድ" ስር "ሆዱ ሻከረ"ን ተመ.

ልቡ ቀረ ቅር አለው፣ ሆዱ አልቆርጥ አለ፣ ሃሳቡ ቀደም ሲል ወደነበረበት ቦታ ተመለሰ።

ልቡ ቆሠሠ ያሰበውን ነገር ለማድረግ ቸኮለ፣ ጓጓ፣ ተነሳሳ።

ልቡ ቆረጠ 1. አንድን ነገር ለማድረግ ወሰነ። 2 እርግፍ አድርጎ ተወ።

ልቡ ቆሰለ 1. በጣም ተናደደ፣ በገነ። 2. በጭቅጭቅ፣ በነገር፣... ብዛት ደከመ ወይም ሰለቸ።

ልቡ ባከነ ሃሳቡ ወዲያና ወዲህ ተበታተነ፣ አንድ ነገር ላይ አልረጋ አለ።

ልቡ ተመለሰ ተረጋጋ።

ልቡ ተሰበረ በጣም አዘነ።

ልቡ ተቃጠለ ተናደደ።

ልቡ ተተረተረ/ትርትር አለ በጣም ደነገጠ።

ልቡ ተነሳ ተቻኮለ፣ አቆበቆበ (አንድ ነገር ለማድረግ፣...)።

ልቡ ተንጠለጠለ 1. ያሰበውን ለማድረግ ወይም ለማግኘት በጉጉት ጠበቀ። 2. ቸኮለ።

ልቡ ተከፈለ 1. ከሁለት ሃሳቦች አንዱን ለይቶ መወሰን ወይም መምረጥ አቃተው፣ አመነታ። 2. ለአንድ ነገር ሙሉ ትኩረት መስጠት አቃተው።

ልቡ ተደፈነ ትእቢተኛ፣ ግጋበኛ፣ አልታዘዝ ባይ ሆነ።

ልቡ ትልቅ ነው 1. ሃሳቡ፣ ምኞቱ ትልቅ ነው። 2. ሃሳቡ፣ምኞቱ ከቅሙ በላይ ነው።

ልቡ ነፈረ "ሆድ" ስር "ሆዱ ነፈረ"ን ተመ.

ልቡ አረፈ ተረጋጋ።

ልቡ አበጠ ተበተ፥ ጥጋብ ተሰማው።

ልቡ አይገኝም/አይታወቅም ምስጢሩ፣ ምኞቱ፥ ሃሳቡ አይታወቅም።

ልቡ አይጠራም "ሆድ" ስር "ሆዱ አይጠራም"ን ተመ.

ልቡ ከዳው ወኔ፥ ድፍረት አጣ።

ልቡ ወለቀ ደከመ፤ ሰለቸ።

ልብ አውልቅ ቅ 1. ነገር የሚደጋግም፣ ችኩ፤ ነዝናዥ፤ አሰልቺ። 2. የተነገረውን የማይሰማ፤ ምክር የማይቀበል።

ልቡ ደረቀ በመጨጨህ፤ በመለፍለፍ ደከመ።

ልቡ ደንደነ ኮራ፤ ታበየ።

ልቡ ገባ ተፅናና፤ ተረጋጋ።

ልቡ ጠራ "ሆድ" ስር "ሆዱ ጠራ"ን ተመ.

ልቡ ጠፋ ዘነጋ፥ ረሳ።

ልቡ ፈሰሰ 1. በጣም ደከመው፥ ዛለ። 2. ሰነፈ።

ልቡ ስንጥቅ አለ ድንግጥ አለ።

ልቡን መታው አቅለሸለሸው፤ አጥወለወለው።

ልቡን ምን በላው/ወሰደው እንዴት ረሳ፥ እንዴት ዘነጋ።

ልቡን ሰወረው አእምሮውን ሳተ።

ልቡን ሰጠው "ሆድ" ስር "ሆዱን ሰጠው"ን ተመ.

ልቡን ቆረቆረው "ሆድ" ስር "ሆዱን ቆረቆረው"ን ተመ.

ልቡን ነሳው 1.አበደ፥ አእምሮውን ሳተ። 2. በአጋጠመው ጥሩ ወይም መጥፎ ሁኔታ ተረጋግቶ ማሰብ አቃተው።

ልቤ አልደነገጠለትም አልሳበኝም፥ አልማረከኝም።

ልቤን ይቆላኛል ከምግብ አለመስማማት የተነሳ ያጥወለውለኛል፥ የህመም ስሜት ይሰማኛል።

ልብ ለልብ ሃሳብ ለሃሳብ። *ልብ ለልብ ይተዋወቃሉ።*

ልብ ሰረቀ 1. ስሜትን ሳበ፤ ማረከ፤ አማለለ። 2. የሌላውን ልብ አሰክዶ፤ አስሸፍቶ፥ የሃሳቡ ደጋፊና ተባባሪ አደረገ።

ልብ ሰቀለ አጓጓ (ፍፃሜውን፥ መጨረሻውን፤ ውጤቱን፥ ቁርጡን፥... ለማወቅ)።

ልብ ሰጠ 1. አደፋፈረ። 2. ማንነቱን፤ ጠባዩን፥ ምስጢሩን፥... ገለጠ፥ አሳወቀ።

ልብ በላ አሳዘነ።

ልብ ነሳ 1. አንገዘገዘ፥ አቃጠለ፥ አሰቃየ። 2. ጨቀጨቀ፥ ነዘነዘ።

ልብ ነካ 1. አሳዘነ። 2. መሰጠ፥ ስሜትን ነካ። 3. አመመ፥ አልስማማ አለ (ምግብ፤ መጠጥ)።

ልብ አለ አስተዋለ፤ አትኩሮ ተመለከተ፥ አጤነ።

ልብ አደረገ አስተዋለ፥ አጤነ።

ልብ አድርግ 1. አማኝ ወይም ምስክር ስለምትሆን ሁኔታውን ተመልከት። 2. ተጠንቀቅ።

ልብ አገኘ 1. ጎበዝ፥ ደፋር ሆነ። 2. ብርቱ፥ ታታሪ ሆነ። 3. ማስተዋል፥ ማመዛዘን ቻለ።

ልብ አጠፋ 1. ስሜትን ያዘ፥ ማረከ። 2. አስረሳ፥ አስዘነጋ። 3. አደከመ።

ልብ ወረደው በጣም ደከመው።

ልብ ይሰልባል ያደክማል። *ፀሃዩ ልብ ይሰልባል።*

ልብ ይጠይቃል ወኔ፥ ድፍረት ይጠይቃል።

ልብ ገዛ 1. ሰከነ፥ ራሱን ተቆጣጠረ። 2. ጠንቃቃ ሆነ።

በልቡ ተኝቷል በደረቱ ተኝቷል።

በልቡ አሰበ "ሆድ" ስር "በሆዱ አሰበ"ን ተመ.

በልቡ ያዘ በአእምሮው መዘገበ፤ አስተዋለ።

በልቡ አደር /አዳሪ እንዳሻው የሚሆን፥ ተቆጣጣሪ የሌለው።

እንደልብ ሆነ /ተገኘ በብዛት ተገኘ።

ከልቡ ሆነ ተረጋጋ።

ከልቡ መከረ አንድን ነገር ለማድረግ፣ ለመወሰን፥ ...አውጣ አወረደ ወይም አሰላሰለ።

ከልቡ አልጣፈውም 1. ከቁም ነገር አልቆጠረውም፥ ናቀው፤ ነገሩም አላለው። 2. ዘነጋው።

ከልብ 1. ከምር፤ የእውነት። *ከልቤ ነው የምነግርህ*፤ 2. በሙሉ ስሜት ወይም ፍላጎት። *ከልብ የተሰራ ስራ ያስታውቃል።*

ከልብ የመነጨ ከእውነተኛ ስሜት ወይም ፍላጎት የመጣ።

የልቡ ሆነለት ያሰበው፥ የተመኘው ተሳካለት ወይም ተፈፀመለት።

የልቡ ደረሰ ያሰበው ወይም የፈለገው ተፈፀመ፥ ተሳካ።

የልቡን ሰራ የፈለገውን ወይም ያሰበውን አደረገ።

የልቡን ተናገረ 1. የፈለገውን ተናገረ። 2. በልቡ ሳምቆ ወይም ደብቆ የያዘውን አውጥቶ ተናገረ።

የልብ ልብ ሰጠው አደፋፈረው።

ልበ ሙሉ ቅ 1. ደፋር፥ ጎበዝ። 2. በራሱ የሚተማመን።

በልበ ሙሉነት በእርግጠኛነት።

ልበ ሙት ቅ ሰነፍ፥ ደካማ፥ ወኔ ቢስ።

ልበ ሰፊ "ሆድ" ስር "ሆደ ሰፊ"ን ተመ.

ልበ ቀላ ቅ 1. ከተቀጠቀጠ በኋላ የሚሰር በሬ፥ በግ፥ ፍየል። 2. ካረጀ ወይም ከመነኩሰ በኋላ የፍትወት ፍላጎት የሚያድርበት (ሰው)።

ልበ ቅን ቅ ደግ፥ ትሁት፥ የዋህ።

ልበ ቆራጥ ቅ የማያወላውል፥ የማያመነታ።

ልበ ቢስ ቅ ዝንጉ፥ ቀልበ ቢስ።

ልበ ብሩህ/ብር ቅ ብልህ፥ አዋቂ፥ ሁሉ ነገር ቶሎ የሚገባው።

ልበ ተራራ ቅ ከአቅሙ በላይ የሚመኝ ወይም የሚያስብ።

ልበ እውር ቅ ብልህነት የሌለው፥ ደደብ።

ልበ ክፍት ቅ ብሩህ አእምሮ ያለው።

ልበ ደንዳና ቅ ብዙ የማይጨነቅ፥ ግድ የሌለው፥ ሃሳብ የለሽ።

ልበ ድንጉጥ ቅ ሩህሩህ፥ የሰው ችግር ቶሎ የሚሰማው።

ልበ ድንጋይ ቅ ጨካኝ፥ የሰው ችግር የማይሰማው።

ልበ ድፍን ቅ 1. ትእቢተኛ፥ ጥጋበኛ፥ አልታዘዝ ባይ። 2. ፍርሃት የማይሰማው። 3. ደደብ፥ ትምህርት ወይም እውቀት የማይገባው።

ልበ ገር ቅ "ሆድ" ስር "ሆደ ገር"ን ተመ.

ልብ ራስ ስ 1. መሃል ራስ፥ አናት። 2. ደረት አካባቢ ያለው የልብ ትርታ የሚሰማበት ቦታ።

ልብ አልባ ቅ ዝንጉ፥ የሚረሳ።

ልብ አውልቅ/አድርቅ/አቅልጥ ቅ 1. ነገር የሚደጋግም፥ ችክ፥ ነዝናዛ። 2. የተነገረውን የማይሰማ፥ ምክር የማይቀበል።

ልብ ወለድ (ልቦለድ) ስ 1. እውነት ያልሆነ የፈጠራ ወሬ፥ በእውነት ያልተፈፀመ። 2. እንደ ረዥም ልቦለድ፥ አጭር ልቦለድ ያለ የፈጠራ ስራ ውጤት የሆነ ስነ ፅሁፍ።

ልብ የለሽ ቅ ዝንጉ፥ ልበ ቢስ።

ልብ ድካም ስ ልብ ተግባሩን በሚገባ ካለመፈፀሙ የተነሳ የሚመጣ የልብ ህመም።

የልብ ቁርጠት ስ ሆድ ቁርጠት።

የልብ ትርታ ስ 1. ልብ ደምን በሰውነት ውስጥ ለማሰራጨት በደቂቃ 70 ያህል ጊዜ የሚያደርገው ምት ወይም ንዝረት። 2. ፍላጎት። *የአንድ አገር መሪ የህዝቡን የልብ ትርታ ለማወቅ ፍላጎቱን ማሟላት ይኖርበታል።*

የልብ ወዳጅ ስ ምስጢር የሚያካፍሉት፥ በጣም የሚያቀርቡትና የሚወዱት ሰው።

የልብ ውጋት ቅ አበሳጭ፥ ነዝናዛ፥ ጨቅጫቃ።

ልባም ቅ 1. አስተዋይ፥ የማይዘነጋ። 2. ባለሙያ።

ልባዊ ቅ ከሙሉ ፍላጎት ወይም ስሜት የመነጨ።

ልቦና (ልቡና) ስ ህሊና ወይም አእምሮ።

ልብሳቢ ስ ከተፈጨ እህል ውስጥ በወንፊት ተለይቶ የሚወጣ የአሰርና የዱቄት ድብልቅ የሆነ እንቅጥቃጭ፥ ጥርግራጊ።

ልብም ስ የመገበሪያ ዱቄት የሚቀመጥበት የሸክላ እቃ።

ልብ አልባ[1] **(ልባልባ፥ ልባልማ)** ስ በሃርና በወርቅ የተጠለፈና ጌጥ ያለው የቀድሞ ጊዜ የሴት ሱሪ።

ልብ አልባ[2] ስ "**ልብ**" ስር ተመ.

ልቦለድ "**ልብ**" ስር "**ልብ ወለድ**"ን ተመ.

ልቦና "**ልብ**" ስር ተመ.

ልቴም ስ የፈንግጣ ጠባሳ።

ልት ስ እንጨቱ ጥንካሬ የሌለው፥ የደረቀ ቀለል ያለሰልሳል የሚባልና ሰዎች ለሆድ መድሃኒት ነው እያሉ እየቀቀሉ የሚበሉት ማላጋነት ያለው የእፅዋት አይነት።

-ልን "**-ለት**"ን ተመ.

ልንቡጥ (ልምቡጥ) ስ ያልተገረዘ የወንድ ብልት፥ ወሸላ።

-ልኝ "**-ለት**"ን ተመ.

ልኡል (ብ.ቁ.ልኡላን) ቅ 1. ከፍ ያለ፥ ከሁሉ በላይ የሆነ። *ልኡል እግዚአብሔር።* 2. የነገስታት ልጆችና ተወላጆች ለሆኑ ታላላቅ መሳፍንት የሚሰጥ የማእረግ ስም።

ልኡካን (ነ.ቁ. ልኡክ) ስ 1. አንድን ጉዳይ ለማስፈፀም በመንግስት ወይም በድርጅት ተወክለው የተላኩ መልእክተኞች። 2. (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) የአለቱ ተረኛ ቀዳሾች።

ልእልት (ብ.ቁ.ልእልታት) ቅ የልኡላን ሚስቶች ወይም የነገስታት ሴት ልጆች የሚጠሩበት የማእረግ ስም።

ልከኛ "**ለካ**[1]" ስር ተመ.

ልክ ዝ.ክ.

ልክፍት "ለከፈ" ስር ተመ.

ልኳንዳ "ሉካንዳ"ን ተመ.

ልደታ ስ የየወሩ የመጀመሪያ ቀን፣ መባቻ። (ልደታ የሚለውን ስያሜ ያገኘው ማርያም የተወለደችበትን ግንቦት 1 ቀንን መነሻ በማድረግ ነው።)

ልደት ስ 1. ታህሳስ 29 (በዘመነ ዮሃንስ ታህሳስ 28) ቀን የሚከበር ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደበት ቀን፤ ገና። 2. ማንኛውም ሰው የተወለደበት ቀን። *ዛሬ ልደቴ ነው።*

ልጃልቅስ (ልጅ አልቅስ) ስ ተዘርዞ ቀሎ ለችግር የሚደርስ የገብስ አይነት።

ልጃገረድ ስ ለአቅመ ሄዋን የደረሰች፣ በድንግልናዋ ያለችና ያላገባች ሴት።

ልጅ ስ 1. ህፃን፣ ጨቅላ፣ በቅርብ ጊዜ የተወለደ። 2. በእድሜ ያልገፋ፣ ወጣት። 3. ያልሸመገለ። *ሊያቴ ገና ልጅ ነው።* 4. ተወላጅ። *እሱ የአዲስ አበባ ልጅ ነው።* 5. የተወለደ፣ ከአብራኩ የወጣ። *ስንት ልጆች አሉህ?* 6. የመሳፍንትና የመኳንንት ወንዶች ልጆች የሚጠሩበት የማእረግ ስም ። *ልጅ ኢያሱ።*

ልጅ በልጅ ሆነ ብዙ ልጆች ወለደ።

ልጅ ነው ያልበሰለ፣ ለጋ ነው።

ልጅ እንደ እናቷ ሆነች ክብረ ንፅህናዋ ተገሰሰ።

ልጅነቱን ያልጨረሰ እድሜው ትልቅ ሆኖ ባህርዩ ወይም ግብሩ የልጅ አይነት የሆነ።

ልጅ እግር ስ ወጣት።

የልጅ ልጅ አየ አያት ሆነ።

ልጅ አልቅስ "ልጃልቅስ"ን ተመ.

ልጉም "ለጎመ" ስር ተመ.

ልጋግ ስ ለሃጭ።

ልጋጋም ቅ (ስድብ) ለሃጫም።

ልጣብ "ለጠበ" ስር "ለጠብ"ን ተመ.

ልጣጭ "ላጠ" ስር ተመ.

ልጥ ዝ.ክ.

ልጦ ዝ.ክ.

ልጨኛ ቅ ትንተ ለሰው በጎ ነገር የሚሰራ፣ ውለታ የሚውል፣ ቁምነገረኛ።

ልጩ "ላጨ" ስር ተመ.

ልፊ (ልፌ) ስ ጥፍረ መጥምጥ።

ልፍጭ ስ ስብነት የሌለው፣ የሚያምለጨልጭና ሊበላ የማይችል ስጋ።

ልፋጫም ቅ (ዘይ.፣ስድብ) የማይደረባ፣ ሃሞተ ቢስ።

ልፋፈ ፅድቅ ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ስርየተ ኃጢአትና ፅድቅ ያስገኛል በሚል እምነት አንዳንድ ሰዎች በቁመታቸው ልክ በብራና አስፅፈው የሚይዙትና የሚፀልዩበት ከሞቱም በኋላ አብሮቻቸው እንዲቀበር የሚደረግ ፅሁፍ።

ልፋፊ "ላፈፈ" ስር ተመ.

ልፌ "ልፊ"ን ተመ.

ሉ የ"ለ" ፊደል ሳብእ ዘር።

ሉሌ ስ አሽከር፣ አገልጋይ፣ ምንደኛ።

ሉል ስ እንጨትነቱ ክብደት ያለውና በወይና ደጋ የሚበቅል ትልቅ ዛፍ።

ሉመለመ ግ ትምክ ትምክ አለ፣ ላላ፣ ሉክሉክ።

ሉሚ ስ 1. እንደ ብርቱካን ያለ ሆኖ መጠኑ አነስተኛ የሆነና ኮምጣጣነት ያለው የሚመጠጥ ወይም የሚበላ የፍራፍሬ አይነት። ሉሚውን የሚያፈራው ተክልም ሉሚ ይባላል። 2. እንደ ሉሚ ክብ የሆነ ተንቀሳቃሽ የጉልበት አጥንት፤ ሉሚታ።

የሉሚ እሸት ስ መጠኑና አይነቱ እንደጠባሻ ሆኖ ሽታውና መአዛው የሚጣፍጥ የእፅዋት አይነት።

ሉሚታ ስ 1. የ"ሉሚ"ን 2ኛ ፍቺ ተመ. 2- በጎራዴ ሰገባ ጫፍ ላይ የሚሰካና ከወርቅ፣ ከብር፣ ... የሚሰራ የሉሚ ቅርፅ ያለው ጌጥ።

ሉምቢ ስ የአሳ አይነት።

ሉተሪ ስ 1. የሉተሪ ትኬት። 2. ተከታታይ ቁጥሮች የተሰጧቸው ብዙ ትኬቶች ለሰዎች ከተሸጡ በኋላ፣ እጣ በማውጣት አሸናፊ ለሆነው ቁጥር የተወሰነለትን ገንዘብ፣ እቃ፣... በመስጠት የሚካሄድ ተግባር።

ሉተሪ ቆረጠ የሉተሪ ትኬት ገዛ።

ሉተሪ ወጣለት 1. የሉተሪ እጣ ደረሰው። 2. ያላሰበውን ጥሩ ነገር አገኘ።

ሉተሪ አዟሪ ስ የሉተሪ ትኬቶችን እያዞረ የሚሸጥ (ሰው)።

የሉተሪ ትኬት ስ የራሱ የሆነ መለያ ቁጥር ያለውና እጣ (ገንዘብ ወይም ሌላ ነገር) ሊያስገኝ የሚችል በገንዘብ የሚገዛ ትኬት።

ሉቲ ስ 1. በቀድሞ ጊዜ አንበሳ ወይም ዝሆን ወይም አውራሪስ፣ ... የገደለ ጀግና ላይ የሚያንጠለጥለው ከወርቅ ወይም ከብር ወይም ከነሃስ፣... የሚሰራ ቀለበት። 2. እንደ ቀለበት ሆኖ ከወርቅ ወይም ከብር፣...የሚሰራ የሴቶች የጆሮ ጌጥ።

ሉክሉክ (ለክለክ) ግ ከመብሰል፣ ከመበስበስ፣...የተነሳ ጥንካሬውን አጣ፣ ትምክ ትምክ አለ፣ ላላ (ፍራፍሬ፣ እባጭ፣...)።

ሉጋ ስ 1. ቅርፁ ሰፋ ያለ፣ ረዥምና

ጠንካራ የሆነ ስር። ቅ 2. (ዘይ.) ቁመናው የሚያምር ረዥም፥ መለሎ (ወጣት)።

ሎጋው ሸቦ 1. ባህላዊ የዘፈን አይነት፣ ሆታ። 2. በሎጋው ሸቦ የሆታ ግጥም ውስጥ በዜማ እየተመላለሰ የሚባል የግጥም አዝማች።

ሎጤ ቅ ሳይጠሩት ወይም ሳይፈልጉት ከተፍ የሚል፣ ቀላዋጭ።

ሎጥ ሎጥ አለ ግ መንደር ለመንደር ዞረ፥ ተንከወከወ።

ሎጥኳጣ ቅ ሳይጠሩት ወይም ሳይፈልጉት ከተፍ የሚል፣ ቀላዋጭ።

ሎፊሳ ስ 1.ፀጉሩ ረዥም የሆነ የበግ ወይም የፍየል ቆዳ። 2. ፀጉሩ ረዥም ከሆነ የበግ ወይም የፍየል ቆዳ የሚሰራ ደበሎ፣ ግላስ፣ ጎፈር።

ሎፍ

ሎፌ ቅ መንደር ለመንደር የሚዞር፣ አውደልዳይ።

ሎፍ ሎፍ አለ ግ መንደር ለመንደር ዞረ፣ አውደለደለ።

ሏ የ"ለ" ራደል ፍንፅቅ ዘር።

መ

መ በዚህ መዝገበ ቃላት ፊደል ተራ መሰረት ከ "ሰ" ፊደል ዘር ቀጥሉ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል (ግእዙ ሆሂ)።

መ- (ከ "አ" ድምፅ በፊት ሲገባ "ማ-" ይሆናል) ከግስ አምድ መነሻ ላይ እየተቀጠለ ስሞችን ወይም አርእስትን ለመመስረት የሚያገለግል ምእላድ። ምሳ. መሰበር /መስራት/ መፃፍ።

መሀር "መከር"ን ተመ.

መሃለቅ ስ 1. የክብደት መለኪያ (ለወርቅ)። 2. ከብረት ነክ ነገሮች ክብ ሆኖ የተሰራና ለመገበያያነት ያገለግል የነበረ የድሮ ገንዘብ።

መሃላ "ማለ" ስር **"ማላ"**ን ተመ.

መሃል "*ማከለ" ስር ተመ.

***መሃረ**

መምህር (ብ.ቁ.**መምህራን**) ስ 1. አስተማሪ ። 2.(ቤ.ክህ.) በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ስርአት መሰረት ለገዳም አስተዳዳሪ የሚሰጥ የማእረግ ስም።

መምህራን ማሰልጠኛ ስ መምህራንን በመምህርነት ሙያ የሚያሰለጥን ተቋም።

መምሬ ስ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ስርአት መሰረት የቅስና ስልጣን ያለው ካህን የሚጠራበት የማእረግ ስም።

ምሁር (ብ.ቁ.**ምሁራን**) ስ በትምህርት፥ በእውቀት አእምሮው የበሰለ ሰው።

ተማረ ግ 1.ትምህርት ቤት ገብቶ ትምህርት ቀሰመ። 2. አወቀ፥ ለመደ፥ ሰለጠነ። ***ምን ተማረ።***

የተማረ ትምህርት፥ እውቀት የቀሰመ፤ ምሁር።

ተማሪ ስ 1. ትምህርት ቤት ገብቶ በመማር ላይ ያለ ሰው። ቅ 2. ለማጅ፥ ተለማማጅ።

ተማሪ ቤት ስ ትምህርት ቤት።

ትምህርት ስ 1. ትምህርት ቤት በመግባት የሚገኝ ወይም የሚቀሰም እውቀት። 2. ከስራ ልምድ፥ ከህይወት ገጠመኝ፥...የሚገኝ እውቀት። *ካለፈው ስህተቱ ትምህርት አግኝቷል።*

ትምህርት ወሰደ/አገኘ አወቀ፥ ተረዳ፥ ተገነዘበ።

ትምህርት ቤት ስ ተማሪዎች በአስተማሪዎች አማካይነት የተለያየ እውቀት፥ ትምህርት የሚቀስሙበት ተቋም።

ተማማረ ግ አንዱ ከሌላው ትምህርት፥ እውቀት፥ ልምድ፥...ቀሰመ።

አስተማረ ግ 1. በትምህርት ቤት ውስጥ ለተማሪዎች ትምህርት ሰጠ። 2. አሳወቀ፥ አሰለጠነ። *ልብስ መስፋት ያስተማራት እሱ ነው።* 3. እንዲማር ረዳ፥ አገዘ። *ያስተማረኝ አጎቴ ነው።*

አስተማሪ ስ 1. በማስተማር ሙያ ላይ የተሰማራ (ሰው)። 2. አለማማጅ፥ አሰልጣኝ።

አስተምህሮ ስ (ፍል.) በተወሰነ የእውቀት ዘርፍ ውስጥ ያለ መሰረታዊ ሃሳብ፤ ትምህርታዊ ይዘት፤ መርህ፤ እምነት፤ ቀኖና።

መሃረብ (መሃረም) ስ ለአፍንጫ፥ ለእጅ፥...ማፅጃ፥ ማበሻ እንዲሆን የተዘጋጀና በኪስ ወይም በቦርሳ የሚያዝ አነስተኛ ጨርቅ።

መሃሪ "ማረ" ስር ተመ.

መሃራ ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) 1. ለሙታን መታሰቢያ ይሆን ዘንድ ተዘጋጅቶ ለካህናት የሚሰጥ ምግብና መጠጥ። 2. ለሙታን መታሰቢያ የሚደረግ ፀሎት።

መሃን "መከነ" ስር **"መካን"**ን ተመ.

መሃንዲስ ስ የህንፃን፥ የድልድይን፥...ስራ የሚቀይስና ስራውንም የሚቆጣጠር ባለሙያ፤ ኢንጂነር።

ምህንድስና ስ የመሃንዲስነት ሙያ ትምህርት።

መሃከለኛ "*ማከለ" ስር **"መካከለኛ"** ን ተመ.

መሃከል "*ማከለ" ስር **"መካከል"** ን ተመ.

መሃይም(ማይም) (ብ.ቁ. **መሃይምናን፤ ማይምናን)** ስ 1. ማንበብና መፃፍ የማይችል ሰው። ቅ 2. (ስድብ) ጠለቅ ያለ እውቀት የሌለው።

መሆዶ(ሞሆዶ) 1. ስ እንደ ሞሰብ ሆኖ ከጭቃ የሚሰራ የእንጀራ ማስቀመጫ። ቅ 2. (ዘይ.) ሆዳም።

***መለለ**

መለሎ ቅ ቀጥ ብሎ ረዘም ያለ።

መለል አለ ግ ቀጥ፥ ረዘም አለ።

መለመለ^{1} ግ ቅጠልን፥ ቅርንጫፍን ከዋናው ግንድ ላይ ቆረጠ፥ ቀነጠበ።

መለመላ ስ እርቃን፥ ራቁትነት።

መለመላውን ቀረ ያለምንም ንብረት ወይም ገንዘብ ባዶ እጁን ቀረ።

ምልማይ ስ ከዛፍ ወይም ከግንድ የተመለመለ ቅጠል ወይም ቅርንጫፍ።

ምልምል ቅ ቅጠሉ ወይም ቅርንጫፉ የተቆረጠ፥ የተመለመለ (ዛፍ፥ ግንድ፥...)።

መለመለ² ግ የሚስማማውን፥ የሚፈልገውን መረጠ (ለአባልነት፥ ለወታደርነት፥...)።

መልማይ ቅ የሚፈለገውንና ተስማሚነት ያለውን ሰው የሚመርጥ፣ መራጭ።

ምልመላ ስ ለአንድ ለተወሰነ ተግባር ወይም ሙያ የሚፈለገውን የሰው ሃይል የመምረጥ ስራ።

ምልምል ቅ 1. ለተወሰነ ተግባር፥ ሙያ የተመረጠ ወይም የታጨ። *ምልምል ወታደር።* 2. ወይዛዝርት በድብቅ የሚይዙት ወጣት የሆነ ወዳጅ።

መለመሌ "**መለመለ¹**" ስር ተመ.

መለሰ ግ 1. አንድን ነገር ቀድሞ ወደነበረበት ቦታ አመጣ ወይም ወሰደ። 2. የተዋሰውን ነገር ለባለቤቱ ሰጠ፥ አስረከበ። 3. ለተጠየቀው ነገር ማብራሪያ ወይም መልስ ሰጠ። 4. ከፈለ። *ውለታ መለሰ።* 5. ከአንድ ቋንቋ ወደ ሌላ ቋንቋ ተረጎመ። *ሉቃን ወደ እንግሊዝኛ የመለሰው ጓደኛዬ ነው።* 6. ደገመ። *ያንኑ እየመለሰ ተናገረ።* 7. ገርበብ አደረገ (በርን፥ መስኮትን)። 8. (ኢ.እ.ተ.ቤ.) አንባቢ አበላሽቶ ሲያነብ መምህሩ ወይም አድማጩ ትክክለኛውን አነባበብ ወይም ቃል ላንባቢው ነገረ። 9. ገታ፥ ከለከለ። 10. አዞረ፥ አቅጣጫውን ቀየረ። *ፊቱን ወደ ምስራቅ መለሰ።* 11. አልቀበል አለ። *ማስረጃው በቂ አይደለም ብሎ መለሰው።*

ከ-(በ) መለስ ከ- ወዲህ። *ከአዋሽ በመለስ*...።

መለስ ቀለስ አለ በተደጋጋሚ መጣ፥ ተመላለሰ።

መለስተኛ ቅ መካከለኛ።

መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ስ የ7ኛና የ8ኛ ክፍል ትምህርት የሚሰጥበት ት/ቤት።

መልስ ስ 1. ለተጠየቀው ጥያቄ የሚሰጥ ማብራሪያ፥ ሃሳብ፥ አስተያየት፥...። 2. ከሄዱበት ወደነበሩበት የመምጣት ክንውን። 3. ሙሽሮች በተጋቡ በሶስተኛው ቀን የሴት ወገኖች የሚያደርጉት ግብዣ። 4. የሴቷም ሆነ የወንዱ ወገኖች ከሰርጉ በኋላ ለሙሽሮች የሚያደርጉት ግብዣ። 5. አንድን የተፈጸመ ድርጊት ተከትሎ የሚከናወን አፀፋዊ ድርጊት። 6. በክፍያ ከተሰጠ ገንዘብ ውስጥ ከሚፈለገው ሂሳብ በላይ ትርፍ በመሆኑ ለከፋዩ ተመላሽ የሚሆን ገንዘብ።

የመልስ ምት ስ (ስፖ.) በእግር ኳስ ጨዋታ ላይ ኳስ በግብ መአዘን አቅጣጫ በተቃራኒው ቡድን ተጫዋች ወደ ውጭ ስትወጣ ጨዋታውን እንደገና ለመጀመር የሚደረግ የኳስ ምት።

የመልስ ጨዋታ ስ (ስፖ.) ሁለት ቡድኖች አንድ ጊዜ ከተጋጠሙ በኋላ እንደገና በሌላ ጊዜና ቦታ የሚያደርጉት ግጥሚያ።

ምልሰት ስ እንደ ስነፅሁፍ፥ ቲያትር፥... ባሉ የፈጠራ ስራዎች ውስጥ ተከታታይነት ያለውን ድርጊት ወይም ታሪክ በመሃል ለተወሰነ ጊዜ በማቋረጥና ወደኋላ በመሄድ ያለፈ ድርጊትን ማሳየት ወይም ያለፈ ታሪክን መተረክ።

ምላሽ ስ 1.የጥያቄ መልስ። 2. ትውኪያ፥ ትፋት፥ ቅርሻት።

ምልስ ቅ 1.ቂም የማይዝ፥ የደረሰበትን በደል ቶሎ የሚረሳ፥ ገር። 2. ቁጣው ቶሎ የሚበርድ።

መለስ አለ ግ 1. ከበፊቱ ሻል አለ። *ንፋሱ መለስ አለ /ሙቀቱ መለስ አለ/ ንዴቱ መለስ አለ።* 2. ገርበብ አለ።

መለስ ያለ ቅ መካከለኛ፥ መጠነኛ የሆነ።

ተመለሰ ግ 1. ቀደም ሲል ወደነበረበት ቦታ መጣ ወይም ሄደ። 2. በትውስት የተወሰደው ነገር እንደገና ለባለቤቱ ተሰጠ፥ ተከፈለ። 3. ለጥያቄው መልስ፥ መፍትሄ ተሰጠ። 4. እንደገና ሆነ፥ ተደረገ፥ ተደገመ። *የጥንቱ ላለማሰ ተመለሰ።* 5. ተስተካከለ፥ ታረመ፥ ደህና ሆነ(ምሳ.ጠባይ)። 6. ቀደም ሲል ያልተቀበለውን አስተያየት፥ እምነት፥...አሁን ተቀበለ፣ አመነ። *ወደ ክርስትና ተመለሰ።*

ተመላሽ ቅ 1. ወደመጣበት ወይም ወደነበረበት የሚመለስ። 2. የተረፈ። *ከከፈልከው ገንዘብ ውስጥ 10 ብር ተመላሽ አለህ።* 3. ለተወሰነ ጊዜ በመያዣነት ተይዞ የሚቆይ(ገንዘብ)።

ተመላለሰ ግ 1. በተደጋጋሚ እየመጣ ሄደ። 2. ንግግር ተለዋወጠ። *ክፉና ደግ ተመላለሱ።* 3. እርስበርስ አንዱ ለአንዱ ሰጠ፥ አደረገ፥ ውለታ፥ ብድር ተከፋፈለ። *ብድር ተመላለሰ።*

ተመላላሽ ቅ ከአንድ ቦታ ወደሌላ ቦታ በቋሚነት እየሄደና እየመጣ አንድን የተወሰነ ተግባር የሚያከናውን።

ተመላላሽ መኪና ስ ከአንድ የተወሰነ ቦታ ወደ ሌላ የተወሰነ ቦታ የሚሄድና የሚመጣ መኪና።

ተመላላሽ ሰራተኛ ስ ቀን ቀን ወደ ተቀጠረችበት ቤት እየሄደች በመስራት ማታ ማታ ለአዳር ወደ ቤቷ የምትመለስ የቤት ሰራተኛ።

ተመላላሽ ተማሪ ስ የአዳሪ ተማሪ ያልሆነ፥ ለቀለቡና ለአዳሩ ወደቤቱ እየተመላለሰ የሚማር ሰው።

ተመላላሽ ታካሚ ስ ሆስፒታል ውስጥ ሳይተኛ እየተመላለሰ የሚታከም በሽተኛ።

አመላለሰ ግ 1. ሰውን፥ እቃን፥...ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ወሰደ፥ አጓጓዘ። 2. በመሄድና በመምጣት እንዲለፋ ወይም እንዲደክም አደረገ (ጉዳዩን ቶሎ ባለመፈፀም)። 3. መልስ ሰጠ፥

አጨቃጨቀ። *የሰውየው አነጋገር የሚያናድድ ነበር፤ ትን ምን ሊመላለሰኝ በማለት ዝም ላሉት።*

ማመላለሻ ስ ማጓጓዣ (በቅሎ፣ መኪና፣ አይሮፕላን፣...)።

አስመለሰ ግ 1. አስታወከ። 2. ተወስዶበት የነበረውን ነገር፣ እቃ ወይም ንብረት እንዲሰጠው አደረገ። 3. በቁማር የተበላውን ገንዘብ መልሶ በላ።

መለሰኛ "ለሰነ" ስር ተመ.

መለሳ ስ ታዛ፣ የእንግዳ ማረፊያ።

መለስተኛ "መለሰ" ስር ተመ.

መለቀሻ "*ለቀሰ" ስር ተመ.

መለበጃ "ለበደ" ስር ተመ.

መለብለቢያ "ለበለበ" ስር ተመ.

መለንቀጫ "ለነቀጠ" ስር ተመ.

መለኛ "መላ" ስር ተመ.

***መለከ**

መለኮት ስ 1. አምላክ፣ እግዚአብሔር። 2. ረቂቅ የሆነ የአምላክ ባህርይ።

መለኮታዊ ቅ አምላካዊ።

ምልኪ ስ 1. አንድን ድርጊት ወይም አጋጣሚ የመጥፎ ወይም የጥሩ ምልክት አድርጎ የመውሰድ እምነት፤ ለምሳሌ ባዶ እንስራ የያዘች ሴት አንድን መንገደኛ አቋርጣው ከሄደች እንደ መጥፎ ምልክት የሚታይ ሲሆን ባንፃሩ ደግሞ ውሃ የሞላ እንስራ የተሸከመች ሴት ካቋረጠችው እንደ ጥሩ ምልክት ይወሰዳል። 2. ለአድባር፣ ለቆሌ፣ ...ቡና ማፍላት፣ ደም ማፍሰስ፣...፤ አምልኮ ባእድ።

ተመለከ ግ ፀሎት፣ ምስጋና፣ መስዋእት ቀረበለት፣ ተሰገደለት፤ ታመነበት።

አመለከ ግ 1. በእግዚአብሔር ታመነ፣ ለእግዚአብሔር ተገዛ። 2. ለጣዖት ሰገደ፣ ተገዛ። 3 (ዘይ.) ተማመነ፣ ተመካ፤ እንደ አምላክ ቆጠረ።

አመለከበት 1.ተማመነበት። 2. አሟረተበት፣ ክፉ ተመኘበት።

ማምለኪያ ስ አምልኮ የሚፈፀምበት ቦታ ወይም የሚመለክበት ነገር።

አምላክ ስ እግዚአብሔር።

አምልኮ(አምልኮት) ስ 1. ለእግዚአብሔር መገዛት፣ መታመን። 2. ለጣኦት፣ ለአድባር፣... መስገድ፣ መገበር።

አምልኮ ባእድ ስ ለጣዖት፣ ለአድባር፣... መገዛት፣ መስገድ።

አምልኮኛ ቅ 1. በቆሌ፣ በውቃቢ፣... የሚያምን፣ የሚያመልክ። 2. እንደ ውሻ ማላዘን፣...ያሉትን ነገሮች እንደ መጥፎ ወይም እንደ ርግብ፣ ንብ፣ ...ያሉትን ነገሮች ደግሞ እንደ ጥሩ ምልክቶች በመውሰድ እንዲህ ይሆናል ብሎ የሚተነብይ ወይም የሚያምን (ሰው)።

***መለከተ**

ምልክት ስ 1.አንድን ነገር ከሌላው ለመለየት የሚያስችል መለያ። 2. አንድን ነገር ለመጠቆም ወይም ለማሳየት፣ ፍንጭ ለመስጠት፣... የሚያገለግል ስእል፣ ፅሁፍ፣ ድምፅ ፣ እንቅስቃሴ፣...።

ምልክት ሰጠ 1. ጠቆመ፣ አሳየ። 2. መለያ አበጀ።

ለምልክት ያህል 1. በጣም በጥቂቱ፣ በትንሹ። 2. ምልክት እንዲሆን።

ተመለከተ ግ 1. አየ። 2. ልብ ብሎ አየ፣ አስተዋለ።

በተመለከተ አስመልክቶ።

ተመልካች ቅ 1. ታዛቢ። 2. ተቆርቋሪ፣ ጠባቂ። 3. ሲኒማን ወይም ቲያትርን ወይም ኳስ ጨዋታን ለመመልከት የሚሄድ ሰው ወይም ህዝብ።

ተመልካች ነው አስተዋይ ነው።

ለሚመለከተው ሁሉ ጉዳዩ ለሚያገባው ሁሉ።

አይመለከተውም አያገባውም።

ተመለካከተ ግ በደንብ ሳይሆን ላይ ላዩን ወይም አለፍ አለፍ ብሎ አየ።

ተመላከተ ግ ከሌላ ቃል ወይም ነገር ጋር ተጣቀሰ።

አመላከተ ግ 1.አሳየ፣ ጠቆመ። 2. አቤቱታ አቀረበ (በፅሁፍ ወይም በቃል)። 3. አሳሰበ፣ አሳወቀ፣ ጠየቀ (በፅሁፍ ወይም በቃል)።

ማመልከቻ ስ አንድን ጉዳይ ለማስፈፀም፣ ለማስታወስ፣... በፅሁፍ የሚቀርብ የጥያቄ፣ የአቤቱታ፣... ደብዳቤ።

ማመልከቻ አቀረበ /ሰጠ በፅሁፍ አመለከተ።

አመልካች ቅ 1. የሚያሳይ፣ የሚያመለክት፣ ጠቋሚ። 2. አቤቱታ አቅራቢ፣ ጠያቂ።

አመልካች ተውላጠ ስም ስ እንደ ይህ፣ ያ፣ እነዚህ፣ እነዚያ፣... ያሉ ተውላጠ ስሞች።

አመልካች ጣት ስ ከእጅ አውራ ጣት ቀጥሎ የሚገኝ ጣት፤ ሌባ ጣት(ስእሉን እጅ ስር ተመ.)።

አመላከተ ግ አሳየ፣ ጠቆመ። *ደህና ማግ መግዛት የምችልበትን ቦታ አመላከተኝ።*

አስመለከተ ግ አሳሰበ፣ አሰኘ፣ አስመኘ።

ምን እንዳስመለከተው እንጃ ቤተ ክርስቲያን አዘውትሮአል።

አስመልክቶ ስለ። *ኢትዮጵያን አስመልክቶ ብዙ መናገር ይቻላል።*

አመለካከት ስ አስተያየት፥ የአስተሳሰብ አቅጣጫ፥ ርእዮተ ዓለም።

መለከት ስ የጥሩንባ አይነት (ስእሉን የሙዚቃ መሳሪያ ስር ተመ.)።

መለኩሴ "መነኮሰ" ስር "መነኩሴ"ን ተመ.

መለኪያ "ለካ^{1}" ስር ተመ.

መለኮስ "መነኮሰ"ን ተመ.

መለኮሻ "ለኮሰ" ስር ተመ.

መለኮታዊ "*መለኮ" ስር ተመ.

መለወጫ "ለወጠ" ስር ተመ.

መለያ "ለየ" ስር ተመ.

መለያያ ዝ.ከ.

መለዮ ዝ.ከ.

መለገ^{1} (መለገገ) ግ ጠባ፥ መጠመጠ (ጡትን)።

መለገ^{2} ግ ሸመቀ፥ አደባ።

መለጎደ ግ መታ።

መለጠ ግ 1. ፀጉርን ላጨ፥ ሙልጭ አድርጎ ነቀለ ወይም ነጨ። 2. ቆዳን፥ ልጥን፥...ገፍፎ አነሳ፥ ላጠ። 3.ፀጉሩ ሙልጭ ብሎ ተነቀለ ወይም ረገፈ፤ መላጣ ሆነ። 4. በእርጩሜ፥ በጅራፍ፥...ገረፈ።

መሊጥ ቅ (ስድብ) ራሰ በራ የሆነ ወይም ፀጉሩ ሙልጭ ብሎ ያለቀ ወይም የተነሳ።

መላጣ ቅ 1.ፀጉሩ ሙልጭ ብሎ የተነሳ። 2. ራሰ በራ። 3. ሳር፥ ዛፍ፥...የሌለበት፥ ገላጣ (መሬት)።

ተመለጠ ግ 1.ተላጨ፤ መላጣ ሆነ። 2. ራሰ በራ ሆነ።

ተመላለጠ ግ ተላላጠ፥ ተገማጠበ፥ ተገሸላለጠ።

መላ ስ ዘዴ፥ ብልሃት።

መላ መታ 1. ዘዴ፥ ብልሃት ፈጠረ። 2. የግምት ወይም የይሆናል አስተያየት አቀረበ፥ ሰጠ።

መላ ቅጡ/ቅዱሱ ጠፋ 1. ስርአት አጣ። 2. ተዘበራረቀ።

መላ ቅጡ ጠፋው 1. ግራ ገባው፥ ተጨነቀ፥ ተምታታበት። 2. የሚሆነውን፥ የሚሰራውን አሳጣው።

መላቅጥ አጣ መላ ቅጡ ጠፋ።

መላ ቅጥ የለውም 1. ስርአት፥ መልክ የለውም። 2. ስራው የማይጨበጥ ነው፥ ውል የለውም።

መላ የለውም 1. ዋጋ፥ ጥቅም የለውም። 2. መፍትሄ የለውም። 3. ስርአት፥ ቅጥ የለውም።

መላ ጣለ 1. ገመተ፥ እንዲህ ሳይሆን አይቀርም አለ። 2. ዘዴ፥ ብልሃት ፈጠረ።

በመላ በግምት፥ በይሆናል።

መለኛ ቅ ብልሃተኛ፥ ዘዴኛ።

መላ ምት ቅ በማስረጃ ያልተረጋገጠ ንድፈ ሃሳብ፥ የግምት አባባል።

መላ ቢስ ቅ 1.ቅጥ ያጣ፥ ስርአት የሌለው። 2. ደንጋራ፥ ዘዴ የለሽ።

መላ ግ ሞላ።

መላ ቅ ጠቅላላ። *መላ ሰውነቴን አሞኛል።*

መላው ሁሉም፥ ጠቅላላው። *መላው የኢትዮጵያ ህዝብ።*

በመላ በጠቅላላ፥ ሁሉም።

መላላጫ "ላጠ^{1}" ስር ተመ.

መላምት "መላ" ስር ተመ.

መላሸ "ላሰ" ስር ተመ.

መላቀቂያ "ለቀቀ" ስር ተመ.

መላቢስ "መላ" ስር ተመ.

መላከ ሞት "መልአክ" ስር ተመ.

መላከ ፅልመት ዝ.ከ

መላው "መላ" ስር ተመ.

መላጅን ስ በቀድሞ ጊዜ ንጉስ ከነሰራዊቱ የሚያርፍበትና ግብር የሚያበላበት ትልቅ ድንኳን።

መላጊያ "ላገ" ስር ተመ.

መላጣ "መለጠ" ስር ተመ.

መልህቅ ስ መርከብ በውሃ ወይም በነፋስ ግፊት እንዳትነዳ ወይም እንዳትንቀሳቀስ ወደ ታች ወጥሮ የሚይዝ መንጠቆ መሰል ከባድ ብረት።



መልህቅ

መልህቅ አነሳ ተንቀሳቀሰ፥ ጉዞ ጀመረ (መርከብ)።

መልህቅ ጣለ ቆመ (መርከብ)።

መልማይ "መለመለ²" ስር ተመ.

መልስ "መለሰ" ስር ተመ.

መልቀሚያ "ለቀመ" ስር ተመ.

መልቀቂያ "ለቀቀ" ስር ተመ.

መልቲ ቅ አታላይ፣ አጭበርባሪ፣ ቀጣፊ።

መልአክ (ብ.ቁ.መላእክት) ስ 1. የፈጣሪ መልእክተኛ፣ አገልጋይ የሆነና የማይሞት ረቂቅ ፍጡር። 2. (ዘይ.) ደግ፣ ሩህሩህ፣ ግብረ መልካም ሰው።

መላከሞት ስ ነፍስን ከስጋ ለመለየት የሚላክ መልአክ።

መላከ ሞት የመሰለ በመክሳቱ፣ በመገርጣቱ ወይም በመጎሳቆሉ የተነሳ ገፅታው የሚያስፈራ (ሰው)።

መላከ ፅልመት ስ የጨለማ መልአክ፤ ሰይጣን።

መልእክተኛ "ላከ" ስር ተመ.

መልእክት ዝ.ከ.

መልከ መልካም "መልክ" ስር ተመ.

መልከ ቀና ዝ.ከ.

መልከ ቢስ ዝ.ከ.

መልከኛ¹ ስ በየገጠሩ ሰፊ ርስት እየተሰጠው ይኖር የነበረ የንጉስ ወገን ወይም ባለሟል።

መልከኛ² "መልክ" ስር ተመ.

መልካ ስ ጥልቀትና አባጣ ጎባጣ የሌለው በመሆኑ ለመሻገሪያ የሚሆን የወንዝ ውሃ የሚያልፍበት ቦታ።

መልክ ስ 1. ፊት ወይም ገፅታ። 2. ውበት፣ ቁንጅና። *መልክ የላትም ቆንጆ ናት።* 3. ቀለም። *መኪናህ መልኩ ምን ዓይነት ነው?* 4. የአንድ ነገር ውጫዊ ገፅታ። 5. በአምስት በአምስት ስንኝ በግጥም የተዘጋጀ የምስጋና ድርሰት።ምሳ.መልከማርያም፣ መልከኢየሱስ፣...።

መልክ አወጣ ቆነጀ፣ አማረ።

መልክ ያዘ ስርአት ያዘ፣ ተስተካከለ።

በመልክ በመልኩ በአይነት በአይነቱ፣ በተገቢው ቦታ።

መልከ መልካም ቅ መልኩ የሚያምር፣ ውብ፣ ቆንጆ።

መልከ ቢስ ቅ መልከ ጥፉ።

መልከ ቀና ቅ ቆንጆ፣ ውብ፣ ሸጋ።

መልከኛ ቅ ቆንጆ፣ ውብ፣ ሸጋ።

መልከጥፉ ቅ የማያምር፣ አስቀያሚ።

መልካም ቅ ጥሩ፣ ማለፊያ፣ ደግ።

መልኬ ጠፋኝ አሁንም አሁንም መልኳን በመስታወት ማየት የምትወድ(ሴት)።

መልክአ ምድር ስ የመሬት አቀማመጥ ወይም ገፅታ።

መልክተኛ "ላከ" ስር "መልእክተኛ"ን ተመ.

መልክአምድር "መልክ" ስር ተመ.

መሎጊያ ስ እቃን በወሳንሳ ለመሸከም የሚያገለግል እንጨት።

መመሪያ "መራ" ስር ተመ.

መመኪያ "*መካ" ስር ተመ.

መሙሊያ "ሞላ" ስር "መሙያ"ን ተመ.

መማለጃ "ማለደ" ስር ተመ.

መማክርት "መከረ" ስር ተመ.

መምህር "*መሃረ" ስር ተመ.

መምሬ ዝ.ከ.

መምቻ "መታ" ስር ተመ.

መምች ዝ.ከ.

መሟጫ "ሟጨ" ስር ተመ.

መረመረ ግ 1. ሃኪም በሽታን፣ የጤንነትን ሁኔታ፣... የተለያዩ የህክምና መሳሪያዎችን በመጠቀም ወይም ታካሚውን በቃል በመጠየቅ ለማወቅ ሞከረ። 2. የተደበቀን ነገር ወይም ምስጢር ለማወቅ ጠየቀ፤ አውጣጣ። 3. አንድን ጉዳይ በደንብ ተመለከተ፣ አጠና፣ አገናዘበ። 4. ፈተሸ፣ ፈተነ። *ለመሻገር ከመሞከርህ በፊት የውሃውን ጥልቀት በዱላህ መርምረው።*

መርማሪ [ፖሊስ] ስ ወንጀል ነክ ጉዳዮችን እየተከታተለ የሚያጣራ የፖሊስ አባል።

ምርመራ ስ 1. በሽታን፣ የጤንነትን ሁኔታ፣...ለማወቅ ሃኪም የተለያዩ የህክምና መሳሪያዎችን በመጠቀም ወይም ታካሚውን በቃል በመጠየቅ የሚያደርገው ጥናት፣ ክትትል። 2. ስለ አንድ ነገር ሁኔታ፣ ምንነት፣...ለማወቅ የሚደረግ ፍተሻ፣ ጥናት።

ምርመራ አደረገ ግ ህክምና አደረገ፣ በሃኪም ታየ።

ምርምር ስ አዲስ ግኝት ለማግኘት ወይም ስለ አንድ ነገር ሁኔታ፣ ምንነት፣ ተፈጥሮ፣... ተጨማሪ መረጃ ለማሰባሰብ የሚደረግ ጥናት።

ተመራመረ ግ 1.የምርምር ስራ አካሄደ። 2. በሃሳብ ተራቀቀ፤ ተፈላሰፈ።

ተመራማሪ ስ የምርምር ስራ የሚያካሂድ ሰው።

አመራመረ ግ 1. አጠያየቀ፣ አፈላሰፈ። 2. አፈላለገ።

ያመራማሪ ስ አንድ እቃ በጠፋ ጊዜ ለአፈላለገ ሰው ወይም አካል የሚሰጥ ገንዘብ

ወይም ሌላ ነገር።

መረመር ስ ውሃ የበረበረው ጉድባ፥ ፈፋ።

መረማመጃ **"ረመደ"** ስር ተመ.

መረረ ግ 1. ጣእሙ እንደ ሬት ወይም እንደ ኮሶ ሆነ። 2.ከረረ (ለነገር)። 3. (ዘይ.) አንገፈገፈ፥ ሰለቸ። *ኑሮ መረረው።*

መራር ቅ የከፋ፥ የጠለቀ። *መራር ሃዘን።*

መራራ ቅ 1. ጣእሙ ሬት ሬት ወይም ኮሶ ኮሶ የሚል። 2. መራር።

መራር ዝ.ከ.

ምሬት ስ 1. ኮሶ ኮሶ ወይም ሬት ሬት የማለት ጣእም።2.(ዘይ.)የመሰልቸት፥ አጥብቆ የመጥላት፥ የመንገፍገፍ ስሜት።

ምር ስ እውነት።

የምር/ከምር የእውነት፥ የቀልድ ሳይሆን።

ተመረረ ግ ሰለቸ፥ ተንገፈገፈ።

ተማረረ ግ 1. ዝ.ከ. 2. ተካረረ፥ የምር ጥል ተጣላ።

አመረረ ግ 1. ቀልዱን የምር አደረገ፥ ተቆጣ። 2. ኮስተር ብሎ.አንድን ነገር ማከናወን ቀጠለ።

አምርሮ ተናገረ በብሶት፥ በብስጭት፥ በቁጭት ስሜት ተናገረ።

አምርሮ አለቀሰ በጣም አለቀሰ።

አማረረ ግ 1. በጣም አዘነ፥ ብሶት አሰማ። 2. አሳጣ፥ ወቀሰ። *ስለደረሰበት ችግር የሚያማርረው ዘመዶቹን ነው።*

አስመረረ ግ 1. አንገፈገፈ፥ አሰለቸ። *ኑሮ አስመረረው።* 2. አበሳጨ፥ አናደደ።

መረሬ ስ ርጥበት ባጣ ጊዜ የሚሰነጣጠቅ ጥቁር አፈር ወይም መሬት።

መረሸት ስ በበቅሎ አንገት የሚደረግ ባለ መርገፍ ጌጥ።



መረሸት

መረሻት ስ በሃር፥ በወርቀዘቦ፥ በጥልፍ የተሸለመና በበቅሎ ኮርቻ ላይ የሚደረግ ባለጌጥ ልብስ።

መረቀ ግ 1. ባረከ፥ ጥሩ ነገር ያስጥህ፥ ያጋጥምህ ብሎ ምኞቱን ገለፀ። 2. የተሰጠህ ስጦታ ይገባሃል፥ የተባረከ ይሁንልህ በማለት አፀደቀለት። *አዲስ የተገዛለትን ልብስ መረቀለት።* 3. ከገዛው ነገር በላይ ሻጭ ለገዢ ተመሳሳይ ወይም ሌላ ነገር ጨምሮ ሰጠ። *ስኳር ሲገዛ ባለሱቁ ከረሜላ መረቀለት።* 4. (ኢ.አ.ተ.ቤ.) ለመምህርነት በቅተሃል ብሎ ማረጋገጫ ሰጠ፥ መሰከረ፥ አስተምር ብሎ ፈቀደ።

መርቆ ከፈተ አንድ የተጋበዘ የክብር እንግዳ አዲስ ተቋም፥ ድርጅት፥ ኤግዚቢሽን፥ ሲሚናር፥...ሲከፈት በሚደረገው ልዩ ስነስርአት ላይ በመገኘት ስራው መጀመሩን ወይም መከፈቱን በይፋ አስታወቀ፥ ገለፀ።

ምረቃ ስ 1. በልዩ ልዩ የትምህርት ተቋሞች ውስጥ የሚሰጡትን የቀለም ወይም የሙያ ትምህርቶችን ላጠናቀቁ ተማሪዎች የምስክር ወረቀት፥ ዲፕሎም፥ ዲግሪ ለመስጠት የሚካሄድ ስነስርአት። 2. አዲስ የተሰራ ቤት፥ ሃውልት፥... ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲታይ ወይም እንዲጎበኝ ሲባል የሚካሄድ ስነስርአት። 3. የወለደን ወይም ከአደጋ የተረፈን ወይም ሌላ ጥሩ ነገር ያጋጠመውን ሰው "እንኳን ደስ አለህ" ወይም "እንኳን አተረፈህ"...ለማለት የሚደረግ ጉብኝት።

ምሩቅ ቅ 1. ቡሩክ። ስ 2. አንድ የተወሰነ ትምህርት ወይም ሙያ ተከታትሎ ያጠናቀቀና የምስክር ወረቀት ወይም ዲፕሎም ወይም ዲግሪ ያለው። *የስነፅሁፍ ምሩቅ።*

ምራቂ ስ 1. ከዋጋ ውጪ ሻጭ ለገዢ (ከገዛው ነገር በተጨማሪ) የሚሰጠው ተመሳሳይ ወይም ሌላ ነገር። 2. (ዘይ.) በውነቱ ቀጭንና አጭር የሆነ ሰው።

ምርቃት ስ 1. በጎ ስራ ለሰራ ሰው "ተባረክ"፥ "እድሜ ይስጥህ" በማለት የሚሰነዘር የመልካም ምኞት መግለጫ። 2. ምራቂ። 3. ምረቃ።

ተመረቀ ግ በቀለም ወይም በሙያ ትምህርት ተቋሞች ውስጥ የሚሰጠውን ትምህርት ተከታትሎ በመጨረሱ የምስክር ወረቀት ወይም ዲፕሎም ወይም ዲግሪ ተሰጠው።

ተመራቂ ስ በቀለም ወይም በሙያ ትምህርት ተቋሞች ውስጥ የሚሰጠውን ትምህርት ተከታትሎ በማጠናቀቅ የምስክር ወረቀት ወይም ዲፕሎም ወይም ዲግሪ ለመቀበል የተዘጋጀ ተማሪ።

አስመረቀ ግ አንድ የትምህርት ተቋም፥ ድርጅት፥...ለማስተማር የተቀበላቸውን ተማሪዎች አስተምሮ ወይም አሰልጥኖ አወጣ።

መረቀነ ግ 1. በጫት ሰከረ። 2. ተመኘ፥ ጓጓ፥ ፈለገ።

ምርቃና ስ ጫት በመቃም የሚመጣ ስካር።

መረቀዘ ግ ውስጥ ውስጡን በጣም ቆሰለ፥ ቂም ያዘ (ቁስል)።

አመረቀዘ ገ.ከ.

መረቅ ስ 1. ስጋ የተቀቀለበት ውሃ። 2. እንደ ስጋ፣ ድንች፣ ዶሮ፣... ያለ ወጥ ፈሳሹ ክፍል። 3- ልብስ የታጠበበት የእንዶድ፣ የሳሙና፣ የአም አረፋ። *በሹራቡ መረቅ ሻሹን አጠበበት።*

ከነመረቁ አጠጣው አጠገቡ ሆኖ ከላዩ ላይ በመደገን ተኩሶ መታው።

መረባርብ "ረበረበ" ስር ተመ.

መረብ ስ 1. ከገመድ ወይም ከክር ጥልፍልፍ ሆኖ የተሰራ የአሳ ማጥመጃ፣ መርበብ። 2. በእግር ኳስ፣ በጠረጴዛ ኳስ፣ በእጅ ኳስ፣ በሜዳ ቴኒስ ጨዋታ ጊዜ በቋሚ እንጨቶች ወይም ብረቶች ተወጥሮ የሚዘረጋ ከክር፣ ከገመድ፣... ጥልፍልፍ ሆኖ የተሰራ የስፖርት እቃ። 3. አንድ ድርጅት ወይም ቡድን አንድን ስራ የሚያከናውንበት ተዋረድ፣ መዋቅር።

መረብ ዘረጋ የአንድን ድርጅት የተለያዩ መዋቅራዊ አካላት መሰረተ፣ አዋቀረ።

መረብ ጣለ አሳ ለማጥመድ መረቡን ወደ ባህር ውስጥ ወረወረ።

መረብ ስራ ስ በክር፣ በገመድ፣...እንደ መረብ ተጠላልፎ የሚሰራ የእጅ ስራ።

መረብ ኳስ ስ (ስፖ.) ግራና ቀኝ በተተከሉ የእንጨት ወይም የብረት ቋሚዎች ላይ በተወጠረ መረብ፣ ስድስት ስድስት ሰዎችን የያዙ ሁለት ቡድኖች፣ ኳስን በእጅ በመቀባበል በመረቡ ላይ አሳልፎ በተቃራኒ ሜዳ ላይ ለማሳረፍ የሚያደርጉት የውድድር ጨዋታ።

መረተ^1 ግ 1.ፍሬው ከእብቅ፣ ከገለባ ተለየ። 2. ብዙ ፍም ወረደ፣ ተንደረከከ።

ምርት ስ 1. በእርሻ፣ በፋብሪካ፣...ተሰርቶ የሚገኝ ማንኛውም ውጤት። 2. እህሉ ተወቅቶ፣ ከእብቅና ከገለባ ተለይቶ የሚገኘው የተጣራ ፍሬ።

ምርታማ ቅ 1. ጥሩ ምርት የሚሰጥ ወይም የሚያስገኝ። 2. ብዙ የስራ ፍሬ የሚያስገኝ፣ ውጤታማ።

ተመረተ ግ 1. ምርት ተገኘ። 2. ተሰራ፣ ተዘጋጀ። *ዘንድሮ ብዙ ጫማ ተመርቷል።*

አመረተ ግ 1. እህልን ዘርቶ፣ አጭዶና ወቅቶ ፍሬ አገኘ፣ አዘመረ። 2. በፋብሪካ ልዩ ልዩ ነገሮችን ሰርቶ አወጣ።

አምራች ስ ምርት በሚያስገኝ ስራ ላይ የተሰማራ ሰው።

ማምረቻ ስ ለምርት ስራ አገልግሎት የሚውል መሳሪያ።

መረተ^2 ግ ዛገ፣ መሬት መሰለ።

መረነ ግ ሞፈርና ቀንበርን በምራን አቆራኘ ወይም አሰረ።

ምራን ስ ሞፈርን ከቀንበር ጋር ማቆራኛ ወይም ማሰሪያ ጠፍር።(ስእሉን ሞፈር ስር ተመ.)።

መረን ቅ ልቅ፣ ባለጌ፣ ስድ።

መረን ለቀቀ ሳይቆጣ ወይም ሳይቆጣጠር ቀረ፣ አባለገ (ልጅን)።

መረን ወጣ ስድ፣ ባለጌ ሆነ።

***መረከዘ**

ምርኩዝ ስ ለመደገፊያነት የሚያገለግል፣ ከብረት ወይም ከእንጨት የሚሰራና ሰዎች በእጃቸው የሚይዙት በትር፣ ከዘራ።

የምርኩዝ ዝላይ ስ (ስፖ.) በረዥም ምርኩዝ በመታገዝ ከተወሰነ ቦታ ላይ ጀምሮ ወደ ሰማይ በመነሳትና በሁለት ቋሚዎች ተደግፎ የተጋደመ ዘንግን ተወርውሮ ለማለፍ የሚደረግ የዝላይ አይነት። የከፍታ ዝላይም ይባላል።

ተመረኮዘ ግ ተረዳ፣ ታገዘ፣ ተደገፈ (በምርኩዝ፣ በመቋሚያ)።

__**ተመርኩዞ**_ምክንያት፣ መነሻ በማድረግ።

አስመረኮዘ ግ እንዲመረኩዝ አደረገ፣ አስደገፈ።

__**አስመርኩዞ** ---ን መነሻ፣ ምክንያት አድርጎ።

መረዋ ስ 1. የቤተክርስቲያን ደውል ወይም ቃጭል። 2. (ዘይ.) ቀጭንና የሚያምር (ድምፅ)።

መረዘ ግ 1. መርዝ አደረገ፣ በመርዝ በከለ። 2. በጣም ጠላ፣ በክፉ ተመለከተ። 3. (ቀለም፣ ቅባት፣...) ከነካው ነገር ላይ እስቅም አለ። *ሻንጣው ውስጥ የነበረው ቀለም ፈስሶ ልብሶቹን መረዛቸው።*

መራዥ ቅ አነጣጣሪ፣ ተኩሶ የማይስት።

መርዝ ስ 1. ሲበላ ወይም ሲጠጣ ወይም ሲሸተት ወይም ሲነካ፣... ህመም ወይም ሞት ሊያስከትል የሚችል ነገር። 2. ለመልቀቅ የሚያስቸግሩ ነገሮችን ለማስለቀቅ እንዲሁም የተለያዩ ነገሮችን ለመቀመም፣... የሚያገለግል ንጥረ ነገር።

መርዘኛ ቅ 1. መርዝ ያለው። 2. ቂመኛ፣ ክፉ። 3. ነገረኛ።

ተመረዘ ግ በመጥፎ ፀባይ ወይም ልማድ፣...ተያዘ፣ ተበከለ፣ ተበላሸ።

መረዳጃ "ረዳ" ስር ተመ.

መረጃ "*ረዳ" ስር ተመ.

መረገ ግ 1. በእንጨት የተሰራን የቤት ግድግዳ በጭቃ ለጠፈ። 2. እንደ እንስራና ጋን ያሉትን የሸክላ እቃዎች አፍ ወይም ሰባራና ሸንቁርን አሸገ፣ ደፈነ። 3. (ዘይ.) የራስን ጥፋት በሌላ አመካኘ፣ አሳበበ። *የራሱን ጥፋት በልጁ ላይ*

መረገበት::

መራጊ ቅ ጭቃ መራጊ፥ ጭቃ ለጣፊ::

መርግ ስ ትልቅ ናዳ::

ምርጊት ስ 1. ከጭድ ጋር ተቦክቶ ከእንጨት በተሰራ የቤት ግድግዳ ላይ የተመረገ ልጥፍ ጭቃ:: 2. ከጭድ ወይም ከገለባና ከሳር ጋር ተደባልቆ ከተቦካ ጭቃ የተበጀ የእንስራ፥ የድብኝት፥... ክዳን:: 3. እንደ እንስራና ጋን ያሉ የሸክላ እቃዎች አፍ ወይም ሰባራና ሽንቁር የተደፈነበት ጭቃ:: 4. (ዘይ.) የማይናገር፥ ዝምተኛ፥ ልጉም::

ምርጊት ፊት ስ ሁልጊዜ ፊቱ ላይ ፈገግታ የማይታይበት ሰው::

ምርግ ቅ 1. የተመረገ:: ስ 2. ገና ያልተለሰነ፥ የጭቃ ልጥፍ ግድግዳ 3. የ"**ምርጊት**"ን 4ኛ ፍቺ ተመ.

ምርግ አለ ግ (ዘይ.) ልጉም አለ፤ ዝም አለ::

መረገተ ግ በጥሬ መታ፤ ደረገመ::

መረገደ ግ በከበሮና በፀናፅል ድምፅ እየታጀበ ከአቋቋም የትምህርት አይነት አንዱ በሆነው በመረግድ የዜማ አወራረድ ስልት አዜመ::

መረግድ ስ ከአቋቋም የትምህርት አይነቶች አንዱ የሆነ በከበሮና በፀናፅል ድምፅ እየታጀበ የሚባል ዜማ::

አመረገደ ግ መረገደ::

መረገገ ግ ጎመዘዘ፥ ኮመጠጠ::

መረጋገጫ "ረገጠ" ስር ተመ.

መረግድ "መረገደ" ስር ተመ.

መረጠ ግ 1. የሚሻለውን፥ የሚስማማውን ወይም የሚፈልገውን ከሌላው ለይቶ አነሳ፤ አወጣ፥ ወሰደ:: 2. ለአንድ አይነት ስራ ወይም ሹመት አጨ፥ ጠቆመ፥ መለመለ::

አይመርጥም 1. አያዳላም፥ አይለይም:: 2. ጥሩም ሆነ መጥፎ ያገኘውን ሁሉ ያግበሰብሳል::

ምራጭ ቅ ከአንድ ነገር ላይ ደህና ደህናው ወይም የተሻለው ተወስዶ የቀረ፤ የማይፈለግ::

ምርጥ ቅ ከሁሉም የሚሻል፤ የሚበልጥ፤ ተፈላጊ::

ምርጫ ስ 1. ከቀረቡት ወይም ካሉት ልዩ ልዩ ነገሮች፥ አማራጮች፥...ተፈላጊውን ወይም ተስማሚውን የመጠቆም ወይም የመምረጥ ተግባር:: 2. ፍላጎት:: *አስተማሪ የሆነው በምርጫው ነው::* 3. ለአንድ ጥያቄ ከሚቀርቡት የተለያዩ መልሶች ተፈታኙ ትክክለኛውን ለይቶ ሊመርጥ ወይም ሊጠቁም የሚችልበት የፈተና አይነት::

ተመረጠ ግ 1.ለአንድ አይነት ተግባር ታጨ:: 2- ከሌላ ነገር ጋር ሲወዳደር የተሻለ ሆኖ ተገኘ::

ተመራጭ ስ ለአንድ አይነት ስራ፥ ስልጣን፥... ብዙ ድምፅ አግኝቶ የተመረጠ ሰው::

ተመርጦ የቀረ ምራጭ::

አማረጠ ግ 1. አወዳደረ፥ አስተያየ፤ የሚሻለውን ለየ:: *የምትፈልገውን አይነት አማርጠህ ግዛ::* 2. ከቀረቡት ነገሮች መሃል ደስ የሚለውን ወይም የሚፈልገውን ለይቶ እንዲወስድ እድል ሰጠ፥ ፈቀደ፥ አስመረጠ::

አማራጭ ቅ በአንድ ነገር ፈንታ በተለዋጭ ሊወሰድ ወይም ሊደረግ የሚችል::

አስመረጠ ግ 1. ከቀረቡት ነገሮች የወደደውን እንዲመርጥ ፈቀደ፤ አማረጠ:: 2. የምርጫ ስነ ስርአት አካሄደ፥ መራ:: 3. ሌላው ሰው እንዲመርጥ አደረገ:: *ለማህበሩ ሊቀመንበርነት ያስመረጠው ጓደኛው ነው::*

አስመራጭ[ኮሚቴ] ቅ የምርጫውን ስነስርአት የሚያካሂድ ወይም የሚመራ አካል::

መሪ "መራ" ስር ተመ.

መሪር "መረረ" ስር ተመ.

መራ ግ 1. ፊት ፊት ሄደ፥ ቀደመ:: 2.ሰጠ(መሬትን):: 3. የተደበቀን፥ የተሰወረን ነገር ወይም እቃ ጠቆመ፥ አሳየ፥ አመለከተ:: 4. ስብሰባን፤ ስራን፤ ጦርነትን፤...በአስተባባሪነት ወይም በበላይነት አካሄደ:: 5. አስተዳደረ፥ ገዛ:: 6. አስተላለፈ፥ ወደ ሌላ አሻገረ (ጉዳይን፥ አቤቱታን፥...):: *ጉዳዩን ወደ አስተዳደር ክፍል መራት::* 7. ሌላው ሰው የሱን ሃሳብ፤ ፍላጎት እንዲከተል አደረገ:: *እህቱ በሱ ሃሳብ እንድትመራ ይፈልጋል::* 8. (ቤ.ክህ.) ተመሪው ከመሪው እየተቀበለ እንዲያዜም መሪው ቀደም ቀደም እያለ ለተመሪው ነገረው:: 9. አይነስውርን ረዳ (እጁን ይዞ መንገድ በማመልከት፥ አብሮ በመጓዝ)::

መሪ ስ 1. ገዢ፥ አስተዳዳሪ፥ የበላይ አዛዥ:: 2. ፊት ፊት ሂያጅ፤ መንገድ የሚያሳይ(ለምሳሌ መንገድ መሪ፥ እውር መሪ):: 3. የመኪና፥ የባቡር፤ የአይሮፕላን፤... አካል የሆነና አቅጣጫውን ለማስያዝ ወይም ለመቀየር የሚያገለግል መዘወሪያ:: 4. (ቤ.ክህ.) በማህሌት ወይም በሌላ የዜማ ስነስርአት ላይ የተወሰኑ ዜማዎችን ወይም ቅኔን ለተመሪው እየነገረ እንዲዜም የሚያደርግ የእለቱ ተረኛ ካህን፤ መዘምር:: 5. ጠቋሚ፥ አመልካች (ለምሳሌ የሌባ መሪ):: 6. አለቃ፥ አስተባባሪ (የቡድን፥ የስራ፥...):: 7. ሰጭ፥ ደልዳይ (ቦታን)::

መሪ ቃል ስ ብዙውን ጊዜ በሃገር መሪ የሚነገርና እንደመመሪያ ወይም መርህ የሚጠቀስ ንግግር::

መሪ ተዋናይ ስ 1. በአንድ ተውኔት ውስጥ አቢዩን ክፍል የሚጫወተው ገፀባህሪይ:: 2.

ቀንደኛ፥ ዋና።

መሪ ጌታ ስ (ቤ.ክህ.) 1. በአንድ ቤተክርስቲያን ውስጥ የሚካሄደውን የዜማ ስርአት በቋሚነት እንዲመራ የተመደበ መምህር። 2. በአንዳንድ የገጠር ቤተክርስቲያን ከማህሌቱ አገልግሎት ስራ በተጨማሪ የአስተዳዳሪነቱን ስራ ደርቦ የሚሰራ የቤተክርስቲያን አለቃ።

ምሪት ስ 1. በመንግስት የተሰጠ መሬት። 2. አንድን የመንግስት ጉዳይ ለማስፈፀም የተላከ ወታደር፥ የመንግስት ባለስልጣን፥ ...በየገበሬው ቤት እየገባ በግዳጅ ይስተናገድበት የነበረ ስርአት።

ተመራ ግ ወታደር ወይም የመንግስት ጉዳይ የሚያስፈፅም ሰው በየገበሬው ቤት እንዲስተናገድ ተሰማራ (በባላባታዊ ስርአት)።

መመሪያ ስ አንድን ስራ ለማካሄድ በቃል የተሰጠ ወይም በወረቀት የሰፈረ ደንብ፥ ትእዛዝ፥ የአሰራር ስልት።

ተመሪ ስ 1.የመሪ ተከታይ፥ ታዛዥ፥ ትእዛዝ ፈፃሚ። 2. መሪው ቀደም ቀደም እያለ የሚናገረውን ዜማ ወይም ቅኔ የሚያዜም መዘምር። 3. ከቦታ ወይም ከርስት መሪ ቦታ ወይም ርስት የተሰጠው፥ ተደልዳይ። 4. በየገበሬው ቤት እየገባ በግዴታ ይስተናገድ የነበረ የመንግስት ባለስልጣን ወይም ወታደር።

አመራ ግ 1. መጣ ወይም ሄደ። *ወደ ቤቱ አመራ።* 2. አዝማሚያ፥ አቅጣጫ ያዘ። *ነገሩ ወዴት እንደሚያመራ አይታወቅም።*

አመራር ስ 1. መመሪያ። *በዚህ ጉዳይ ላይ አመራር ተሰጥቶበታል።* 2. የመንግስት፥ የፖለቲካ ድርጅት፥...የበላይ አካል። *አመራሩ ያሳለፈው ውሳኔ ተቀባይነት አላገኘም።*

መራራ "መረረ" ስር ተመ.

መራር ዝ.ክ.

መራዥ "መረዘ" ስር ተመ.

መራጃ ስ የድንጋይ መፍለጫ ትልቅ መዶሻ።

መራጊ "መረገ" ስር ተመ.

መሬት ስ 1. ለፀሃይ ባላት ቅርበት ሶስተኛ፥ በመጠን ከፕላኔቶች አምስተኛና ከዘጠኙ አለማት (ፕላኔቶች) አንዷ የሆነች የምንኖርባት አለም፥ ምድር (በተጨማሪ ፕላኔት ስር ተመ.)። 2. አፈር፥ የብስ የሆነውና ውሃ ያልተኛበት ክፍል። 3. የቤት ወለል።

መሬቱ (ማሳው) ለስልሷል እየተደጋገመ ታርሷል።

መሬቱ ጦም አደረ ሳይዘራበት ከረመ።

መሬት ለቀቀ 1.ወደላይ ከፍ አለ፥ አየር ላይ ሆነ። 2. ታበየ፥ ተንቀባረረ።

መሬት ነው ቻይ፥ ታጋሽ ነው።

መሬት አታሟሽም ለመሞት የመጀመሪያው ሰው አትሆንም።

መሬት ከዳው አዙሮት ወይም አንሸራቶት ድንገት ሳያስበው ወደቀ።

መሬት ያዘ ተስተካክሎ ተቀመጠ።

መሬት ይቅለለው አንዳንድ ሰዎች የሟች ዘመዳቸውን ወይም ወዳጃቸውን ስም በሆነ ምክንያት በሚያነሱበት ጊዜ (የመቃብር ጭንቅ ይቅለልለት፥ መሬት አትክበደው ለማለት) የሚናገሩት የበጎ ምኞት አባባል።

መሬት ጠበበው 1. በጣም ተደሰተ፥ ፈነደቀ። 2. በጣም ተጨነቀ፥ አዘነ፥ የሚያደርገው አጣ።

መሬት ጠብ አይልም ሳይፈፀም፥ ሳይደርስ አይቀርም (ርግማኑ፥ የተናገረው)።

ከመሬት ተነስቶ ያለምንም ምክንያት።

ከመሬት ደባለቀ መሬት ላይ ክፉኛ ጣለ፥ አፈረጠ።

መሬት ቅርቡ ቅ 1. ድንክ። 2. ቁጭ ማለት የሚወድ፥ ሰነፍ። 3. ቶሎ ቶሎ የሚወድቅ።

የመሬት መንቀጥቀጥ ስ ድንገተኛና ሃይለኛ የሆነ የመሬት መንቃነቅ፥ መናወጥ።

የመሬት ምላስ ስ ሾጠጥ ያለና ወደ ባህር ገባ ብሎ የሚገኝ መሬት፥ ልሳነ ምድር።

የመሬት ስሪት የ"ስሪት"ን 2ኛ ፍቺ ተመ.

መርሃ ሰሜን ስ የ"ኮምፓስ"ን ፍቺ ተመ.

መርሃ እውር ስ የጨረቃ፥ የፀሃይ፥ የቀን፥ የወር፥ የአመት፥ የዘመን አቆጣጠር ያለበት መፅሃፍ።

መርሃ ግብር ስ በቅደም ተከተል የተዘጋጀ እቅድ፥ ፕሮግራም።

መርህ ስ መመሪያ።

መርማሪ "መረመረ" ስር ተመ.

መርቄ "ሜርቆ"ን ተመ.

መርበብተ ሰለሞን ስ አጋንንትን አጥምዶ ለመያዝና በቁጥጥር ስር ለማድረግ ያስችላል ተብሎ የሚነገርለት አስማት ወይም ድግምት።

መር አለ "እመር" ስር "እመር አለ"ን ተመ.

መርከብ ስ በነዳጅ ሃይል የሚንቀሳቀስና በመጠን ከጀልባና ከታንኳ የሚበልጥ፥ ሰውን፥ እቃን፥...በባህር ላይ ለማመላለስ የሚያገለግል የውሃ ላይ መጓጓዣ (ስእሉን መጓጓዣ ስር ተመ.)።

መርከብ አዛዥ ስ በመርከብ ላይ የመርከብ ሃላፊ ሆኖ የሚሰራ ሹም።

መርከበኛ ስ 1. መርከብ ነጂ። 2. በመርከብ ላይ የሚሰራ ሰው።

መርዘኛ "መረዘ" ስር ተመ.

መርዝ ዝ.ከ.

መርዱ "*ረዳ" ስር ተመ.

መርዱፋ (መርዱፉ) ስ አቡጀዲ የሚመስል ወፈር ያለ ቆርፋዳ ጨርቅ::

መርገም "ረገመ" ስር ተመ.

መርገጥ "ረገጠ" ስር ተመ.

መርገጫ ዝ.ከ.

መርገፍ "ረገፈ" ስር ተመ.

መርግ "መረገ" ስር ተመ.

መርጦ ስ ሸርጥ፥ ግልድም (ሃረር አካባቢ የሚነገር)::

መርፌ ስ 1.በአንደኛው ጫፍ በኩል ሹል የሆነ፥ በሌላው ጫፍ በኩል ደልዳም ያለ ሆኖ የክር ማስገቢያ ቀዳዳ ያለውና ለልብስ መስፊያ የሚያገለግል ቀጭን ብረት፤ የእጅ መርፌ:: 2. ስሪንጅ ላይ ተሰክቶ ፈሳሽ የሆነ መድሃኒትን በውስጡ ወደ ህመምተኛው ሰውነት ለማስተላለፍ የሚያስችል ቀጭን ብረት:: 3. ተንቀሳቃሽ ተሰኪ የሆነ፥ በሸክላ ላይ የተቀረፀውን ድምፅ ተቀብሎ የሚያስተላልፍ፥ ጫፉ ሹል የሆነ ኤሌትሮኒክስ የሸክላ ማጫወቻ እቃ::

መርፌ ነኝ መድሃኒት በመርፌ እየወሰድኩ ስለሆነ ይህንን አልበላም ወይም አልጠጣም ለማለት የሚነገር አባባል::

መርፌ ቁልፍ ስ አንዱ ጫፍ ሹል ሆኖ ሁለተኛው ትይዩ ጫፍ ደግሞ እንደክዳን ወይም እንደ መቆለፊያ ሆኖ እንዲያገለግል የተሰራና ልብስ ማያያዣነት የሚጠቅም መርፌ::



መርፌ ቁልፍ

የመርፌ እራት ስ መርፌው እንዳይጠፋ ወይም ከተቀመጠበት ቦታ በቀላሉ እንዲገኝ በመርፌው ቀዳዳ ላይ የምትንጠለጠል ትንሽ ክር::

መሮ ስ ለእንጨት ወይም ለድንጋይ መቦርቦሪያ፥ መሰርሰሪያ ወይም መጥረቢያ የሚያገለግል ጫፉ ሹል ወይም ስል የሆነ ብረት::



መሮ

መሰለ ግ 1. በመልክ፥ በመጠን፥ በባህርይ፥... ከሌላ ጋር አንድ ሆነ፤ ተቀራረበ:: 2. አበረ፥ ተስማማ:: 3.አብሮ ሆነ ወይም አብሮ አደረገ፥ ተቀላቀለ:: 4. በምሳሌ ተናገረ::

ለይምሰል የውሸት፤ ለይስሙላ::

ምን የመሰለ በጣም ቆንጆ፤ በጣም ጥሩ፥ ደስ የሚል፥ የሚያረካ::

ምን ይመስልሃል? ምን አስተያየት አለህ?

እንደሚመስለኝ እንደገባኝ፤ እንደተሰማኝ::

እንዲህ አይምሰልህ አንድ ነገር ከሚገመተው በላይ (ጥሩ ወይም መጥፎ) መሆኑን ለመግለፅ የሚነገር አባባል::

የመሰለኝን 1. ያሻኝን፥ የፈለግሁትን:: 2. የታየኝን፤ የተሰማኝን፥...::

የማይመስል ነገር መደረጉ፥ መፈጸሙ፥ እውነትነቱ የሚያጠራጥር ነገር::

ይህን የመሰለ 1. ከዚህ ጋር የሚቀራረብ፥ እንዲህ ያለ:: 2. ጥሩ፥ ግሩም፥ መልካም የሆነ::

መሰል ቅ 1.የሚመስል:: *አረንጓዴ መሰል ቀለም ተቀብቷል::* 2. አምሳያ፥ ተወዳዳሪ:: *ለክፋቱ መሰል የለውም::*

__መሳይ ቅ 1.__የሚመስል:: *ጨዋ መሳይ::* 2. የሆነ:: *ነገረኛ መሳይ::*

መስሎ አዳሪ 1. ከሁሉ የሚስማማ፥ የሚግባባ:: 2. ተለማማጭ::

ምሳሌ ስ 1. ቀደም ሲል የተነገረን ነገር ለማጠናከርና የበለጠ ግልፅ ለማድረግ የሚቀርብ ሃሳብ፥ ማብራሪያ፥...:: 2. አርአያ:: *መሪዎች የጥሩ ስነምግባር ምሳሌ መሆን ይጠበቅባቸዋል::*

ምሳሌያዊ አነጋገር ስ ቀደም ሲል የተነገረን ነገር ለማጠናከር፥ ይበልጥ ግልፅ ለማድረግና ለዛ ለመስጠት ሲፈለግ በንግግር ላይ ተጨማሪ ሆኖ የሚቀርብ አጭር አባባል::

ምስል ስ 1. በፎቶግራፍ ተነስቶ ወይም በውሃና በመስታወት ውስጥ ተንፀባርቆ የሚታይ የአንድ ነገር መልክ:: 2. በድንጋይ፥ በእንጨት፥ በወርቅ፥...ላይ የተቀረፀ የአንድ ነገር መልክ:: 3. የመስቀል ቅርፅ ባለው እንጨት ላይ የሟችን ልብስ በማልበስ በለቅሶ ጊዜ ለማልቀሻነት የሚያገለግል ቅርፅ::

ምስለ ቢስ ቅ መልከ ጥፉ::

ምስል አፍሳሽ ስ ወርቅ፥ ብር፥... እያቀለጠ የተለያዩ ቅርፃቅርፆችንና ጌጣጌጦችን የሚሰራ::

ምስያ ቅ አምሳያ::

ተመሰለ ግ የሌላ ነገርን መልክ፥ ገፅታ፥ ባህርይ ያዘ::

ተምሳሌት ስ በጥሬው ካለው ትርጉም ውጪ ሌላ ነገርን የሚወክል ቃል ወይም ሃረግ:: *አንበሳ የጀግና ተምሳሌት ነው/ጨለማ የመከራ ተምሳሌት ነው::*

ተመሳሰለ ግ በመልክ፣ በመጠን፣በባህርይ፣... ተቀራረበ፤ አንድ ሆነ።

ተመሳሳይ ቅ በመልክ፣ በመጠን፣በባህርይ፣... የተቀራረበ፣ አንድ የሆነ።

ተማሰለ ግ ተደበላለቀ፤ ተቀላቀለ፣ ተዋሃደ።

አመሰለ ግ በሌላው ላይ ክፉ ተመኘ (ሳይተኩስ ጠመንጃ ደገነበት፣ ሳይመታው ዱላ ቃጣበት)።

አያምስልና እውነት አያደርገውና፣ አያድርስና።

አመሳሰለ ግ 1. ተመሳሳይ፣ ተቀራራቢ ወይም አንድ አይነት አደረገ። *በሬት ከተሰራው ጋር አመሳስለህ ስራልኝ።* 2. አነፃፀረ፣ አወዳደረ። *ኢትዮጵያንና አሜሪካን በኢኮኖሚ ደረጃ ማመሳሰል አይቻልም።*

አማሰለ ግ አደበላለቀ፣ አቀላቀለ፣ አዋሃደ።

ማማሰያ ስ ወጥ፣ ገንፎ፣...ሲሰራ ለማማሰል የሚያገለግል አጠር ቀጠን ያለ እንጨት።

አምሳል ስ የአንድ ነገር ተመሳሳይ፣ አምሳያ፣ ምሳሌ።

አምሳያ ቅ በመልክ፣ በቀለም፣...ሌላውን የሚመስል፣ ከሌላው ጋር የሚመሳሰል። *አምሳያ ልጁ ናት።*

አስመሰለ ግ 1. ያልሆነና ያልተደረገ ነገርን እንደሆነ፣ እንደተደረገ አድርጎ አቀረበ። 2. ተመሳሳይ፣ ተቀራራቢ፣ አንድ አይነት አደረገ።

አያስመስልብህና አያምጣብህ፣ አያድርስብህና (ክፉ ነገር)።

አስመሳይ ቅ ያልሆነውንና ያልተደረገውን እንደሆነ፣ እንደተደረገ አድርጎ የሚያቀርብ ውሸታም፣ አታላይ።

መሰለቂያ "ሰለቀ" ስር ተመ.

መሰላል ስ ከፍ ወዳለ ቦታ (ቤት፣ ዛፍ፣...) ላይ ለመውጣትና ለመውረድ የሚያገለግሉ ደረጃ መሰል መረጋገጫዎች ያሉት ባለሁለት ወይም ባለአራት እግር እንጨት፣ ብረት፣ ገመድ፣...።

መሰላል

መሰል "መሰለ" ስር ተመ.

መሰረተ ግ አቆመ፣ ተከለ፣ አቋቋመ።

መሰረት ስ 1. ከላይኛው የመሬት ክፍል በታች የሚሰራ የቤት፣ የህንፃ፣ የግንብ፣...መነሻ፣ መቆሚያ። 2. ውጥን፣ ጅምር። *ነገሩ የተበላሸው ገና ከመሰረቱ ነው።*

መሰረት ጣለ ጀመረ። *ዳግማዊ አፄ ምኒልክ ለኢትዮጵያ የዘመናዊ ስልጣኔን መሰረት የጣሉ መሪ ናቸው።*

መሰረተ ልማት ስ ለአንድ አገር ልማት በተቀዳሚነት አስፈላጊ የሆነ እንደመንገድ፣ የትምህርት፣ የጤና ተቋም ያለ የህብረተሰቡ መገልገያ።

መሰረተ ቢስ ቅ ተጨባጭ ማስረጃ ወይም እውነትነት የሌለው። *መሰረተ ቢስ ወሬ።*

መሰረተ ትምህርት ስ ለመሃይምናን የሚሰጥ የመጀመሪያው የቀለም ትምህርት።

የመሰረት ድንጋይ ስ አንድ ድርጅት፣ ተቋም፣...ሊሰራ በታቀደበት ቦታ ላይ የተጋበዘው የክብር እንግዳ በመጀመሪያ የሚያኖረውና ለዚሁ ጉዳይ ተብሎ የተዘጋጀ የድንጋይ ምልክት።

መሰረታዊ ቅ ዋና፣ በጣም አስፈላጊ፣ ከሁሉም የሚቀድም።

መሰረታዊ ለውጥ ስ ስር ነቀል ለውጥ።

መስራች ጉባኤ [ስብሰባ] ስ አንድን ድርጅት፣ ማህበር፣... ለማቋቋም የሚደረግ የመጀመሪያ ስብሰባ።

ምስረታ ስ አንድን ድርጅት፣ ማህበር፣... የማቋቋም ተግባር።

መሰሪ (መሰርይ) ቅ በጣም ተንኮለኛ፣ ሸረኛ።

መሰርሰሪያ "ሰረሰረ" ስር ተመ.

መሰስ አለ ግ ቀስ፣ ዝግ ብሎ ሄደ ወይም መጣ።

*መሰቀለ

ምስቅልቅል ቅ ዝብርቅርቅ፣ ውጥንቅጥ፣ የተመሰቃቀለ።

ምስቅልቅል አለ ግ ተዘበራረቀ፣ ቅጥ አጣ፣ ተደበላለቀ።

ተመሰቀለ ግ ተደበላለቀ፣ ቅጥ አጣ።

አመሰቃቀለ ግ አወሳሰበ፣ አደበላለቀ፣ ቅጥ አሳጣ።

አመሳቀለ ግ አደባለቀ፣ ቅጥ አሳጣ።

*መሰቃ

መስቃ ስ የጡር፣ የግፍ ንግግር። *ተመችቶኛል ብለህ መስቃ አትናገር።*

ተመሰቃ ግ ተመፃደቀ።

መሰቅሰቂያ "ሰቀሰቀ" ስር ተመ.

መሰብሰቢያ "ሰበሰበ" ስር ተመ.

*መሰነ

መሰነች ግ መከነች፣ አልወልድ አለች(ለቀንድ ከብት)።

መሲና ስ የማትወልድ (ላም፣ በግ፣...)።

መሰናክል "ሰነከለ" ስር ተመ.

መሰናዘሪያ "ሰነዘረ" ስር ተመ.

መሰናዶ "*ሰነዳ" ስር ተመ.

መሰንቆ "ማሲንቆ"ን ተመ.

መሰንበቻ "ሰነበተ" ስር ተመ.

መሰከረ ግ ስላየው፥ ስለሰማው፣ ስለሚያውቀው ነገር ወይም ድርጊት እውነተኛውን ሁኔታ በቃል ወይም በፅሁፍ አረጋገጠ፣ አስረዳ።

ምስክር ስ 1. አንድ ድርጊት ሲፈፀም በቦታው ተገኝቶ ያየ ወይም የሰማ ሰው፤ እማኝ። 2. ስለአየው፥ ስለሰማው፥ ስለሚያውቀው ነገር ህጋዊ በሆነ ቦታ ቀርቦ በመሃላ ቃሉን የሚሰጥ ሰው፤ እማኝ። 3. እንደ ድጓ፥ ቅዳሴ ያሉ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የሚሰጡ ትምህርቶችን ለማስተማር የሚችሉ መምህራንን አስተምሮ ስለብቃነታቸው ማረጋገጫ (የምስክር ወረቀት) የሚሰጥ የመምህራን መምህር (ለምሳሌ የድጓ ምስክር)።

ምስክር ቆጠረ 1. አንድ ድርጊት ሲፈፀም በቦታው የነበሩትን ሰዎች እገሌ፣ ልብ በሉ፣...አለ። 2. እማኝ ጠራ፤ ምስክሮቼ እነ እገሌ ናቸው ብሎ ተናገረ (ለሽማግሌ ወይም ለዳኛ)።

የምስክር ወረቀት ስ 1. አንድን የሙያ ወይም የትምህርት ዘርፍ ተከታትሎ ላጠናቀቀ ግለሰብ፥ በሰለጠነበት መስክ ብቁ መሆኑን ለመግለፅ፥ ህጋዊነት ወይም ስልጣን ባለው አካል የሚሰጥ የፅሁፍ ማስረጃ። 2. ለአንድ ነገር እንደ ማስረጃ ወይም ማረጋገጫ የሚያገለግል የፅሁፍ ማስረጃ።

ተመሳከረ ግ ተያየ፥ ተነፃፀረ፥ ተገናዘበ።

አስመሰከረ ግ 1. ድርጊቱን፥ ማንነቱን፥ ችሎታውን አሳየ ወይም አሳወቀ። 2.(ቤ.ክህ.) በተማርከው ትምህርት የሚፈለገውን ችሎታ አግኝተሃል፥ ልታስተምር ትችላለህ የሚል ፈቃድ አገኘ፤ ማስረጃ ተሰጠው። *ድጓ አስመስክሯል።*

መሽክ ስ 1. የሳርን፥ የቡቃያን ስር የሚበላ ነጭ ትል። 2. (ዘይ.) ሀ. ተንኮለኛ፣ ምስጥ። ለ. ቢበላ የማይጠግብ።

መሰገ ግ 1. አጎረ። 2. ሰገሰገ፥ ሰካ። 2. ከግጦሽ በኋላ አንድ ቦታ ላይ በመሰብሰብ እንዲተኙ አደረገ (እንደ በግና ፍየል ያሉ የቤት እንስሳትን)።

ምሳግ ስ ከብቶች ሳር ከበሉ በኋላ ተሰብስበው የሚተኙበት ከቤት ውጪ ያለ ቦታ።

*መሰገነ

ምስጉን ቅ 1. የተመሰገነ። 2. ጥሩ መስራቱ የታወቀና የተደነቀለት። *ምስጉን ሰራተኛ።*

ምስጋና ስ ጥሩ ለሰራ፥ ውለታ ለዋለ፥... የሚቀርብ ሙገሳ፥ ውዳሴ።

ምስጋና ይግባው ይሞገስ፥ ይወደስ፥ ይመስገን፤ ምስጋና ይድረሰው፣ መመስገን ይገባዋል።

ምስጋን ይንሳው 1.ሁለት የተለያዩ ነገር ግን የሚመሳሰሉበት ባህርይ ያላቸውን ነገሮች በማነፃፀር አንዱ ከሌላው ይበልጣል ለማለት የሚነገር አባባል። *ውይ! በርበሬው ሲያቃጥል! ሚጥሚጣን ምስጋን ይንሳው።* 2. ምስጋና አይገባውም፥ ምስጋና ያሳጣው።

ምስጋና ይድረሰው ምስጋና ይግባው፥ ምስጋና ለእሱ ይሁን።

ምስጋና ቢስ ቅ 1. የማያመሰግን፤ ውለታ ቢስ። 2. መልካም ስራ ሰርቶ ምስጋና የማይሰጠው፣ የማያገኝ (የመቆርቆር አነጋገር)።

ምስጋና የለሽ ቅ 1. የማያመሰግን። 2. ውለታ ውሉ የማይመሰገን፥ ምስጋና የማያገኝ ወይም የማይሰጠው (የመቆርቆር አነጋገር)። *ምስጋና የለሽ መሆኑን ባውቅም ደግ ነገር ከመስራት ወደ ኋላ አላልም።*

ተመሰገነ ግ ተሞገሰ፥ ተመረቀ፥ ተባረከ።

ተመስገን ምስጋና ይድረስህ፤ ምስጋና ለአንተ ይሁን (ለእግዚአብሄር)።

አመሰገነ ግ ምስጋና አቀረበ፤ አሞገሰ፥ አወደሰ፤ መረቀ፣ ባረከ።

መሰጠ ግ ትኩረት ሳበ፤ ሃሳብ ወሰደ።

ተመሰጠ ግ በሃሳብ ርቆ ሄደ፤ ትኩረቱ ተሳበ።

ተመስጦ ስ ልዩ የአእምሮ ትኩረት።

*መሰጠረ

ምስጢር(ሚስጥር) ስ 1. ይፋ ያልሆነ ነገር፥ ድብቅ ጉዳይ። 2. በቅኔ ውስጥ ሰምና ወርቁ የያዘው ትርጓሜ፥ ፍሬ ነገር። 3. (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) በቤተክርስቲያን ቅፅረ ግቢ በተለይ ቤተልሄም እየተባለች በምትጠራው ቤት ውስጥ የሚከናወን ተግባር (የስርአተ ቁርባን ዝግጅት)።

ምስጢር አወጣ ድብቅ የነበረን ነገር ይፋ አወጣ፤ ገለጠ።

ምስጢር አየ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ድቁና ከተቀበለ በኋላ በቤተክርስቲያን ቅፅረ ግቢ በምትገኘውና ቤተልሄም ተብላ በምትጠራው ቤት ውስጥ የሚከናወን ተግባር አየ፤ ተረዳ፥ አወቀ።

ምስጢር ጠበቀ ምስጢር የሆነን ነገር ለማንም ሳያሳውቅ፤ ሳይናገር ቀረ፤ ደብቆ ያዘ።

ምስጢረ ስላሴ ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) የስላሴን የአንድነትና የሶስትነት ምስጢር የሚያስረዳ ትምህርት።

ምስጢረ ስጋዌ ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ስለአምላክ (ክርስቶስ) ሰው የመሆንና ስጋ የመልበስ ምስጢር የሚያስረዳ ትምህርት።

ምስጢረኛ ስ የልብን የሚነግሩት ወይም

የሚያዋዩት የቅርብ ወዳጅ፣ ጓደኛ።

ምስጢር ኪስ ስ በወንድ ሱሪ ፊት ለፊት በቀኝ በኩል ያለ ትንሽ ኪስ።

ተመሳጠረ ግ 1. በድብቅ ወይም በስውር፥ በምስጢር ተነጋገረ፥ ተመካከረ። 2. አንድ ትንኮል ወይም መጥፎ ነገር ለመፈፀም በስውር ተመካከረ፤ አሴረ።

አመሰጠረ ግ ስውር ወይም ሽፍን የነበረውን ሃሳብ ገለፀ፤ አብራራ(ቅኔ)።

መሰጥ ስ በእህያ ወይም በአጋሰስ ሆድ አካባቢ የሚውልና በጀርባቸው ላይ የተጫነውን ስደንብ ለማሰርና ለማጥበቅ እንዲያመች ሆኖ ታጥፎ ወረድ ያለ የመጫኛ መጥለፊያ።

መሲህ ስ የተቀባ ንጉስ ወይም ካህን ወይም ነቢይ።

መሲና "መሰነ" ስር ተመ.

መሳ ቅ አቻ፥ እኩል።

መሳ ለመሳ (መሳ በመሳ) እኩል በኩል።

መሳለሚያ "*ሰለመ" ስር ተመ.

መሳል "ሳለ^{2}" ስር ተመ.

መሳሪያ "ሰራ^{1}" ስር ተመ.

መሳቂያ "ሳቀ" ስር ተመ.

መሳቢያ "ሳበ" ስር ተመ.

መሳድ ስ በቁቲት ውስጥ ያለች የሸማ መወጠኛ ቀጭን እንጨት (ስእሉን ሸማኔ ስር ተመ.)።

መሳፍቻ "ወሳፍቻ"ን ተመ.

መሳፍንት ስ (ነ.ቁ. **መስፍን**) በቀድሞ ጊዜ ከንጉሱ ጋር በዝምድና የተሳሰሩና በስልጣን ላይ የነበሩ የገዥው መደብ አባላት።

መስህብ ስ የሚማርክ ወይም የሚስብ ሀብት ያለው ነገር (ቅርሳቅርስ፣ መልክአምድር፥...)።

መስመር "*ሰመረ" ስር ተመ.

መስሪያ ቤት "ሰራ^{1}" ስር ተመ.

መስቀለኛ "ሰቀለ" ስር ተመ.

መስቀል ዝ.ክ.

መስቀያ ዝ.ክ.

መስቃ "*መሰቃ" ስር ተመ.

መስቆር "ሰቆረ" ስር ተመ.

መስቀርት ዝ.ክ.

መስበቂያ "ሰበቀ" ስር ተመ.

መስተ- በአንዳንድ ቃላት ላይ ባእድ መነሻ በመሆን እየተቀጠለ እርስ በርስ የ—የሚል ፍቺ የሚሰጥ ምእላድ፤ ***መስተዋድድ፥ መስተፋቅር፥...***።

መስተሃድርት (መስታድርት) ስ የጠፉ ከብትን አውሬ እንዳይበላው እየተባለ የሚደገም አስማት ወይም ድግምት።

መስተባርር "በረረ" ስር ተመ.

መስተንግዶ "*ነገደ" ስር ተመ.

መስተአምር በቃላት መጨረሻ እየገባ ነገሩ (ቃሉ) ቀደም ሲል የተጠቀሰ መሆኑን የሚያሳይ ምእላድ መጠሪያ። *መጽሃፉ (መፅሃፍ·ኡ)*። መፅሃፍ የተባለው ቃል ቀደም ሲል የተጠቀሰ መሆኑን የሚያመለክተው መስተአምራዊ ምእላዱ "ኡ" ነው።

መስተዋት(መስታወት) ስ 1. መልክን ወይም ከፊት ለፊቱ ያለውን ምስል መልሶ የሚያሳይና ልሙጥ ሆኖ ውሃ መልክ ያለው እቃ። 2. ብርሃን ማስተላለፍ የሚችል፤ ብዙውን ጊዜ በመስኮትና በር ላይ የሚገጠም፥ ጠጣር ሆኖ ግን በቀላሉ ሊሰበር የሚችል የህንፃ መሳሪያ እቃ።

መስተዋት መሰለ በጣም ፀዳ፥ አማረ።

መስተዋድድ በስምና ስም እከል በሆኑ ቃላት መነሻ ወይም በመነሻና መድረሻ ላይ እየገባ የነገሮችን ዝምድና የሚያመለክት የንግግር ክፍል። (ምሳሌ ወደ፣ ከ...ጋር፣ በ...ላይ)።

መስተዳድር "አደረ" ስር ተመ.

መስተፃምር በግስ ላይ እየተጨመረ ግሱ እንዲያስር የሚያግድ እንዲሁም ቃላትን፥ ሃረጎችን፣ አረፍተ ነገሮችን የሚያያይዝ የንግግር ክፍል። *ላበበና ከበደ ከተዋወቁ ጀምሮ አንደተፋቀሩ ኖሩ*። (መስተፃምሮቹ ከ፣ ና፣ እንደ፣ ናቸው)።

መስተፋቅር ስ ወንድና ሴትን ወይም ሰዎችን እርስበርስ ያፋቅራል የሚባል አስማት ወይም መድሃኒት።

መስቲካ (ማስቲካ) ስ ከሙጫና ከሌሎች ቅመሞች የሚሰራ መጣበቅነት ያለው የሚታኘክ ጣፋጭ።

መስታድርት "መስተሃድርት"ን ተመ.

መስኖ ስ 1. ከወንዝ፥ ከምንጭ፥... ተጠልፎ ሰው ሰራሽ የሆነ መንገድ ወይም ቦይ ተበጅቶለት ለእርሻ ስራ የሚውል ውሃ። 2. ከወንዝ፣ ከምንጭ፣... ውሃን በቦይ ወይም በሌላ ዘዴ በመጥለፍ መሬትን ውሃ እያጠጡ የሚካሄድ የግብርና ስራ ወይም ዘዴ። 3. በመስኖ የሚለማ ወይም የለማ መሬት።

የመስኖ መሬት/እርሻ ውሃገብ የሆነ ወይም የመስኖ ውሃ ያለው መሬት፤ እርሻ።

የመስኖ ውሃ (ዘይ.) የራሱ የሆነ ጠንካራ አቋም የሌለው፤ በሌላ ሰው ሃሳብ የሚመራ (ሰው)።

መስአ ስ በሰሜንና በምስራቅ መካከል ያለ የአለም ማእዘን አቅጣጫ (በተጨማሪ ማእዘን ስር ተመ.)።

መስከረም ስ የአመቱ የመጀመሪያው ወር ስም።

መስከረም ጠባ የመስከረም ወር ገባ፥ ተጀመረ።

መስክ ስ 1. በለምለም ሳር የተሸፈነ ሰፊ ሜዳ፥ መሬት። 2. የመስክ ስራ።

መስክ ወጣ የመስክ ስራን ለማከናወን ሄደ።

የመስክ ስራ ስ የተለያዩ ጥናቶችንና ምርምሮችን የሚያካሂድ ሰው ወይም የቢሮ ሰራተኛ ከመደበኛ የስራ ቦታው ርቆ በመሄድ የሚያከናውነው ጥናት፥ ስራ።

መስኮት ስ በቤት ግድግዳ ወይም በተሽከርካሪዎች ጎን ላይ ለአየርና ለብርሃን መግቢያ እንዲሆን የሚሰራና ብዙውን ጊዜ መዝጊያ ያለው ክፍት ቦታ (ስእሉን ቤት ስር ተመ.)።

መስዋእት "ሰዋ" ስር ተመ.

መስጊድ ስ የሙስሊሞች ቤተ ፀሎት።

መስፈሪያ "ሰፈረ^1" ስር ተመ.

መስፈርት ዝ.ክ.

መስፍ ስ እንደማረሻ፥ ቢላዋ፥...ያሉ የተለያዩ መሳሪያዎችን የሚሰሩ ባለሙያዎች ተፈላጊውን የብረት ቁራጭ ካጋሉ በሗላ በላዩ ላይ አጋድመው የሚቀጠቅጡበትና ልዩ ልዩ ቅርፅ የሚያወጡበት ጠፍጠፍ ያለ ትልቅ ብረት።

መስፍን "መሳፍንት"ን ተመ.

መሶብ ስ ከአክርማና ከሰንደዶ የተሰፋ ለእንጀራ ማስቀመጫ ወይም ለመብያ የሚሆን የቤት እቃ (ስእሉን የስፌት እቃ ስር ተመ.)።

መሶብ ወርቅ ስ ልዩ ልዩ ቀለማት ባላቸው አለላዎች ተጊጦ የተሰፋና ረዘም ያለ እግር ያለው መሶብ (ስእሉን የስፌት እቃ ስር ተመ.)።

መሸ ግ ጨለመ፥ ማታ ሆነ።

መሸ በከንቱ ፍሬ ያለው ነገር ሳይሰራ፥ በከንቱ ሲያውደለድል ወይም በጉደለሽነት ጊዜውን የሚያሳልፍ ሰው።

መሸ አዳሪ ስ ቋሚ መኖሪያ የሌለውና በደረሰበት ቦታ የሚያድር ሰው።

ምሽት ስ ከፀሃይ ጥልቀት በሗላ ጨለማ እስኪሆን ያለው ጊዜ።

አመሸ ግ እስከ ምሽት ወይም እስከ ማታ ወይም እስከ ሌሊት ቆየ።

ማምሻ ስ 1. የመኝታ ሰአት እስኪደርስ ለማንደድ የሚለቀም የማገዶ እንጨት (ብዙውን ጊዜ በገጠር አካባቢ)። 2. ምሽት። 3. መቆያ፥ የምሽቱን ጊዜ ማሳለፊያ።

ማምሻውን ወደ ማታ ገደማ። *ማምሻውን ወደ ከተማ ብቅ ብሎ ነበር።*

አመሻሽ ስ ምሽት።

አስመሸ ግ እስከምሽት ወይም እስከ ማታ ወይም እስከ ሌሊት አቆየ።

መሽለቀ "ሞሽለቀ"ን ተመ.

መሸቢያ "ሸበበ" ስር ተመ.

መሸተ ግ ለገበያ የሚሆንና የሚሸጥ ጠላ፥ ጠጅ ወይም አረቄ፥... ጠመቀ፥ አዘጋጀ።

መሸታ ስ 1. ለሽያጭ የተዘጋጀ ጠላ ወይም ወይም አረቄ። 2. ቶሎ ለገበያ እንዲደርስ ተብሎ ያለጥንቃቄ የተሰራ መናኛ እቃ፥ ልብስ፥...።

መሸታ ቤት ስ እንደ ጠላ፥ የአገር አረቄ፥ ጠጅ ያሉ መጠጦች የሚሸጡበት ቤት።

መሸተኛ ስ 1. ጠላ ወይም ጠጅ ወይም የአገር አረቄ፥... እያዘጋጀች የምትሸጥ ሴት። 2. መሸታ ቤት አዘውትሮ በመሄድ የሚጠጣ (ሰው)።

መሸንገያ "ሸነገለ" ስር ተመ.

መሸኛ "ሸኘ" ስር ተመ.

መሸከ ግ 1. ደቀቀ፥ ነከተ። 2. ተጥመለመለ፥ ተልወሰወሰ።

እምሽክ አለ ግ ስብርብር፥ ድቅቅ አለ።

አመሸከ ግ 1. ደቋቆሰ፥ አነኳኮተ። 2. ጥርግ፥ ሙጥጥ ወይም እንክት አድርጎ በላ።

መሸገ ግ 1. ከጠላት ጦር ለመከላከል ጉድጓድ በመማስ፥ ድንጋይ በመካብ፥...መሸሸጊያ አበጀ፤ ምሽግ ሰራ። 2. ተደበቀ፥ ተሸሸገ። 3. (ዘይ.) በአንድ ቦታ ወይም አካባቢ ተወስኖ ተቀመጠ ወይም አዘውትሮ ተገኘ።

ምሽግ ስ 1. ከጠላት ጦር ለመከላከል ጉድጓድ በመማስ፥ ድንጋይ በመካብ፥... የሚሰራ መከለያ ቦታ፥ ተገን። 2. (ዘይ.) ሁልጊዜ የማይጠፋበት ቦታ፥ መገኛ፥ መዋያ። *የእገሌ ምሽግ ያ ጠጅ ቤት ነው።*

ምሽግ ሰበረ ምሽግን ጥሶ ገባ፥ አለፈ።

ተመሸገ ግ ተከለለ፥ ተደበቀ፥ ምሽግ ውስጥ ሆነ።

መሸጋገሪያ "*ሻገረ" ስር ተመ.

መሸጎሪያ "ሸጎረ" ስር ተመ.

መሸፈኛ "ሸፈነ" ስር ተመ.

መሹለኪያ "ሾለከ" ስር ተመ.

መሹለክለኪያ ዝ.ክ.

መሸረብ (መትረብ) ስ 1. የውሃ ቱቦ። 2. አሸንዳ።

መሸቀቅ ስ በሱሪ፥ በቀሚስ፥...ወገብ ዙሪያ የሚገባ ማሰሪያ፤ ጥብጣብ።

መሿለኪያ "ሾለከ" ስር ተመ.

መቀመቅ (መቅ) ስ በጣም ጥልቅ የሆነ ጉድጓድ፤ አዘቅት።

መቀመቅ ወረደ ሲኦል ገባ።

መቀመጫ "*ቀመጠ" ስር ተመ.

መቀራቅር "ቀረቀረ" ስር ተመ.

መቀራቅርት"ቀረቀረ" ስር "**መቀራቅር**"ን ተመ.

መቀርሰሚያ ስ የአረቄ መጠጫ፤ መለኪያ።

መቀርቀሪያ "ቀረቀረ" ስር ተመ.

መቀርቀቢያ "ቀረቀበ" ስር ተመ.

መቀርጠፊያ "ቀረጠፈ" ስር ተመ.

መቀስ ግ በመቀስ ቆረጠ ወይም ቀደደ።

መቀስ ስ እጀታ ያሳቸው ሁለት ትይዩ የሆኑ ስለታም ብረቶችን በማገጣጠም የተሰራ መቁረጫ፣ መቅደጃ፣ መከርከሚያ፤ መቁረጪት።

መቀስ

መቀስ ምት ስ ወደ ላይ በመዝለልና እግርን እንደ መቀስ በማሰባጠር በአንደኛው እግር የሚመቱ አስመስሎ በሁለተኛው እግር የሚመታ የእግር ኳስ አመታት።

መቀስ ቅድ ስ አንገትጌው እንደባላ ከስር ጠበብ ከላይ ሰፋ ብሎ የወጣ የልብስ ቅድ።

መቀቀያ "ቀቀለ" ስር ተመ.

መቀነስ "ቀነሰ" ስር ተመ.

መቀነሻ ዝ.ከ.

መቀነት "*ቀነተ" ስር ተመ.

መቀነቻ ዝ.ከ.

መቀናጀ "*ቀንጀ" ስር ተመ.

መቀንደቢያ "ቀነደበ" ስር ተመ.

መቀንጠቢያ "ቀነጠበ" ስር ተመ.

***መቀኘ**

ምቀኛ ስ ሌላው ሰው ጥሩ ነገር እንዲያገኝ የማይፈልግ፣ የማይወድ ወይም እንዳያገኝ የሚጥር ሰው።

ተመቀኘ ግ 1. ለሌላው ጥሩ ነገር እንዳይደረግለት ተመኘ አደረገ፤ ተከላከለ። 2. ሌላ ሰው ባለው ወይም ባገኘው ጥሩ ነገር ያላግባብ ቀና።

መቀየሪያ "ቀየረ" ስር ተመ.

መቀየጃ "ቀየጀ" ስር ተመ.

መቀንጠቢያ "ቀጠበ" ስር ተመ.

መቀጣጫ "ቀጣ" ስር ተመ.

መቀጫ ዝ.ከ.

መቀጮ "ቀጣ" ስር "**መቀጫ**" ን ተመ.

መቀፍቀፊያ "ቀፈቀፈ" ስር ተመ.

መቁሊያ "ቆላ" ስር ተመ.

መቁረርት "ቆረረ^1" ስር ተመ.

መቁረጪት "ቆረጠ" ስር ተመ.

መቁረጫ ዝ.ከ.

መቁነን "ቆነነ" ስር ተመ.

መቁያ "ቆላ" ስር "**መቁሊያ**"ን ተመ.

መቁጠሪያ "ቆጠረ" ስር ተመ.

መቂናጥ ስ 1.በሶስት በኩል በክር የተያያዘና በሽመና ስራ ጊዜ መኑ ከፍ ዝቅ እንዲል የሚያደርግ እንጨት። 2. ሞሳሳ ሆኖ እንደዘንግ የተሰራና በቱቦ መሰል ብረት ውስጥ ገብቶ በአንጻች አይነት ግፊት ወደላይና ወደታች እየተንቃነቀ እንቅስቃሴን የሚሰጥ የሞተር አካል።

መቃ ስ ቅጠሉ ሻካራ፣ ቀጫጭንና ረዣዥም፤ ግንዱ አንጓ ያለውና ውስጡ ክፍት የሆነ የእፅዋት አይነት፤ ሸንበቆ።

መቃ ልቅም ስ በመቃ ስንጥር እየተለቀመ የሚሰራ የሸማ ጥበብ አይነት።

መቃ መስዬ ስ እንደመቃ ያለ ግን ከመቃ የሚቀጥንና የሚጠነክር የእፅዋት አይነት።

መቃ ብእር ስ ከመቃ ተቀርፆ የተዘጋጀና ቀለም እየተጠቀሰበት የቁም ፅሁፈት ለመፃፊያ የሚያገለግል ብእር።

መቃረቢያ "ቀረበ" ስር ተመ.

መቃብር "ቀበረ" ስር ተመ.

መቃን ስ በቤት በር ወይም መስኮት ግራና ቀኝ ጎበኑን ተሸክሞ የቆመ እንጨት (ቤት ስር የበርን ስእል ተመ.)።

መቃኛ ስ 1. አንድ ቤተክርስቲያን ተሰርቶ እስከሚያልቅ ድረስ ታቦቱ የሚቆይበት ጊዜያዊ ቤት። 2. አንድ ትልቅ ቤት ተሰርቶ እስከሚያልቅ ድረስ አጠገቡ የሚሰራና በጊዜያዊነት የሚያገለግል ትንሽ ቤት።

መቃወሚያ "*ቀወመ" ስር ተመ.

መቃድ ስ 1. ጫፉ ወደ ደንደሉ በኩል ቆለፍ ያለ የብረትና፣ የቆርበት መፋቂያ ቢላዋ። 2. የመነኩሴ መታጠቂያ፤ ሰቅ።



መቃድ 1ኛ ፍቺ

መቃጠሪያ "*ቀጠረ^{2}" ስር ተመ.

መቃጥን ስ የአሳ ማጥመጃ መንጠቆ::

መቄ [ወፍ] ስ በብዛት ሆኖ የሚበር ብዙውን ጊዜ በመቃ ላይ ጎጆ ሰርቶ የሚኖር ቢጫ ወፍ::

መቅ "መቀመቅ"ን ተመ.

መቅለምት "ወቅለምት"ን ተመ.

መቅመቆ ስ ሰፋፊና ለስላሳ ቅጠል ያለው፣ ስሩ ቢጫ የሆነና ቅቤ ሲነጠር ቀለሙን ቢጫ እንዲያደርገው የሚጨመር አነስተኛ የእፅዋት አይነት::

መቅረዝ ስ ሻማ፣ ጧፍ፣...በላዩ ላይ ተሰክቶ ለማያዝ የሚያገለግል ከሸክላ፣ ከብረት፣ ከነሃስ፣...የሚሰራ የማብሪያ እቃ፣ ቀንዲል::

መቅረዝ

መቅረጫ "ቀረፀ" ስር ተመ.

መቅሰፍታም "ቀሰፈ" ስር ተመ.

መቅሰፍት ዝ.ከ.

መቅኒ (**መቅን**) ስ እንደቅልጥም ባሉ ክፍት አጥንቶች ውስጥ የሚገኝ የአጥንት ቅባት::

መቅኖ ስ እርባና፣ በረከት::

መቅኖ ቢስ እርባና፣ በረከት የሌለው::

መቅኖ የለውም አይበረክትም::

መቅዘፊያ "ቀዘፈ" ስር ተመ.

መቅደስ "ቀደሰ" ስር ተመ.

መቅድም "ቀደመ" ስር ተመ.

መቅጃ "ቀዳ" ስር ተመ.

መቅጫ "ቀጣ" ስር ተመ.

መቆለፊያ "ቆለፈ" ስር ተመ.

መቆሚያ "ቆመ" ስር ተመ.

መቆርቆሬት "ቆረቆረ" ስር ተመ.

መቆስቆሻ "ቆሰቆሰ" ስር ተመ.

መቆናቆን "ቆነቆነ^{3}" ስር ተመ.

መቆናጠጫ "ቆነጠጠ" ስር ተመ.

መቆንጠጫ ዝ.ከ.

መቆያ "ቆየ" ስር ተመ.

መቆጣጠሪያ "ቆጠረ" ስር ተመ.

መቆፈሪያ "ቆፈረ" ስር ተመ.

መቋሚያ "ቆመ" ስር ተመ.

መቋረፊያ ስ ካህናት የሚለብሱት እጅ ሰፊና ደረተ ክፍት ቀሚስ::

መቋቋሚያ "ቆመ" ስር ተመ.

መቋደሻ "*ቆደሰ" ስር ተመ.

መቋጠሪያ "ቋጠረ" ስር ተመ.

መበለት "እመበለት"ን ተመ.

መበለቻ "በለተ" ስር ተመ.

መበያ "በላ" ስር "ማባያ"ን ተመ.

መባ "መብአ"ን ተመ.

መባቻ "ባተ" ስር ተመ.

መብል "በላ" ስር ተመ.

መብረቅ "በረቀ" ስር ተመ.

መብሩቅ ስ በጥራቱ ከአቡጀዲና ከመርዱፋ በጣም የሳቀ ዘመናዊ ነጭ ጨርቅ::

መብራት "በራ^{1}" ስር ተመ.

መብሻ "በሳ" ስር ተመ.

መብት ስ 1. አንድ ሰው ወይም አካል በአንድ ነገር ወይም ጉዳይ ላይ የሚፈልገውን ለማድረግም ሆነ ላለማድረግ የሚያስችለው ስልጣን::2. አንድ ሰው አስፈላጊ ሆኖ ሲያየው ሊያገኘው የሚገባ ነገር፣ አገልግሎት፣ ጥቅም፣...::

መብቱ ተገፈፈ በሰብአዊነት ወይም በህግ ያገኘው መብት ሳይከበርለት ቀረ::

መብቱን አስከበረ መብቱን አስጠበቀ::

መብቱን አስጠበቀ በሰብአዊነቱ ወይም በህግ ያገኘው መብት ህጋዊ በሆነ ወይም በሌላ መንገድ ተጠቅሞ፣ በሌላ ሰው ወይም አካል እንዳይደፈር ወይም እንዳይነጠቅ አደረገ::

መብትና ግዴታ ስ አንድ ሰው ወይም አካል ያለው መብትና ከእርሱ የሚጠበቅ ግዴታ::

የመብት ጥያቄ ስ በሰብአዊነት ወይም በህግ የተገኘን ወይም ሊገኝ የሚገባን መብት አስመልክቶ የሚቀርብ ጥያቄ::

መብአ(**መባ**) ስ እንደ ጧፍ፣ እጣን፣ ዘቢብ፣...ያለ ለቤተክርስቲያን የሚሰጥ ስጦታ::

መተለገ ግ 1. ቆነጠጠ:: 2. ራበ፣ ሞረሞረ:: 3. ነጠቀ፣ ሞሸለቀ::

መተሳለፊያ "አለፈ" ስር ተመ.

መተማመኛ "አመነ" ስር ተመ.

መተረ^{1} ግ መጥኖ ቆረጠ፣ ከተፈ(ስጋን)::

መተሮ (**አምቃሮ**) ስ የተከተፈ ስጋ::

መተረ^{2} ግ ርዝመትን ለካ::

ሜትር ስ የርዝመት መለኪያ (1 ሜትር 100 ሴንቲ ሜትር ይሆናል)::

ሜትር ኩብ ስ ርዝመቱ፥ ጎኑና ጥልቀቱ አንድ አንድ ሜትር የሆነ ማንኛውም ነገር።

ሜትር ካሬ (ካሬ ሜትር) ስ የስፋት መለኪያ (ርዝመቱ 1 ሜትር፥ ጎኑም 1 ሜትር የሆነ የስፋት መጠን፤መሬብ ሜትር።

መተሬቻ "ተረተ" ስር ተመ.

መተሬ ስ ፍሬው የከሰ መድሃኒት ነው ተብሎ የሚበላ እንደ ሃረግ ያለ የእፅዋት አይነት።

መተርከሻ "ተረከሰ" ስር ተመ.

መተሮ "መተረ¹" ስር ተመ.

መተተ ግ መተት አደረገ ወይም አስደረገ።

መተት ስ በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ለማድረስ ወይም መተት አድራጊው የሚፈልገው ነገር እንዲፈፀምለት በማለት በተለያዩ ነገሮች ማለትም እንደ ልብስ፥ ምግብ፥ የቤት ቁሳቁሶች በመሳሰሉት ላይ የሚደረግ ድግምት።

መተተኛ ስ በሰው ላይ መተት የሚያደርግ ወይም የሚያስደርግ ሰው። 2. (ዘይ.) ጉዳዩን ለማስፈፀም ብዙ ጊዜ የሚሳካለት፤ ከተም ሰው ገር የሚሆንለት።

መተከዣ "ተከዘ" ስር ተመ.

መተኪያ "ተካ" ስር ተመ.

መተኮሻ "ተኮሰ"ስር ተመ.

መተያያ "አየ" ስር **"መታያ"** ን ተመ.

መተጻደሪያ "አደረ" ስር ተመ.

መታ¹ ግ 1. ደበደበ፥ ገረፈ፥ ገጨ። 2. በጥይት አቆሰለ ወይም ገደለ። 3. ለጋ፥ ጠለዘ (ኳስን)። 4. በጠበጠ፥ ደባለቀ፥ አዋሃደ (ተልባን፥ እንቁላልን፥...)። 5. ደረደረ፥ ከረከረ፥ ተጫወተ (በገናን፥ ክራርን፥ ማሲንቆን፥...)።

መታ ያለ አጠር ና ወፈር ያለ።

መምቻ ስ በድር መሃከል የሚያልፈው ማግ እንዲጠጋጋ ወይም ልሰቅ እንዲል የሚመታበት የሸማኔ እቃ።

መምች ስ 1. እንደ ብይ፥ አዝራር፥ ቆርኪ ባለ የቁማር ጨዋታ ለመምቻነት ተመርጦ የሚያገለግል ብይ፥ አዝራር፥...። 2. እንደ "ሰኛ ማከለኛ" ባለ የልጆች ጨዋታ ላይ እየተወረወረ ለመጫወቻ የሚያገለግል የሸክላ ስባሪ ወይም ትንሽ ጠፍጣፋ ድንጋይ።

ምት ስ 1. መቶ አመታት። 2. በግጥምና በግጥም መሰል ስራዎች ላይ የሚታይ የቀለም ወይም የፊደል አመጣጠን።

ምች ስ ቅባት ያለው፥ የሚሸት ምግብ፥... ነካክቶ ወይም ላብ ካሳበ በኋላ ለፀሃይ በመጋለጥ ምክንያት ይመጣል የሚባል የበሽታ አይነት።

ምች መታው የምች በሽታ ያዘው።

[የ] ምች መድሃኒት ስ የምችን ህመም ያድናል ተብሎ ከልዩ ልዩ ቅጠላ ቅጠሎች የሚዘጋጅ መድሃኒት።

ተመታ ግ ተሸነፈ፥ ተደመሰሰ (ለምሳሌ በጦርነት)።

ተማታ ግ 1. መታ፥ ደበደበ። 2. ተምታታ።

ተምታታ ግ 1. ተዘበራረቀ፥ ተደበላለቀ። 2. ተሳከረ፥ ተሳሳተ፥ ተወነባበደ።

አማታ ግ 1. አጭበረበረ፥ አታለለ። 2. አዘበራረቀ፥ አደበላለቀ። 3. ምች ተጠናወተ፥ አመመ። *ታልቅ በልተህ ላትታጠብ አትውጣ ያማታሃል።*

አምታታ ግ 1. አጭበረበረ፥ አታለለ። 2. አዘበራረቀ፥ አደበላለቀ።

አምታች ቅ አጭበርባሪ፥ አታላይ።

መታ² ግ ሰረረ (አህያ፥ ፈረስ፥...)።

መታረሪያ ስ ጥጥ በሚነደፍበት ጊዜ ደጋኑን ደገፍ ለመያዝ የሚያገለግል ቀጭን እንጨት (ስእሉን ደጋን ስር ተመ.)።

መታሰቢያ "አሰበ" ስር ተመ.

መታቀፊያ "አቀፈ" ስር ተመ.

መታወቂያ "አወቀ" ስር ተመ.

መታያ "አየ"ስር ተመ.

መታጠቂያ "ታጠቀ"ስር ተመ.

መታጠቢያ "አጠበ" ስር ተመ.

መት ስ መደዳ፥ ረድፍ።

መትረብ "መሸረብ"ን ተመ.

መትረየስ ስ በተከታታይ ብዙ ጥይቶችን በአንድ ጊዜ ሊተኩሱ ከሚችሉ የጦር መሳሪያዎች አይነት አንዱ።

መቶ ስ 1. በዘጠና ዘጠኝና በመቶ አንድ መካከል ያለ ቁጥር መጠሪያ፤በአሃዝ ሲፃፍ 100፥፻ ነው። ቅ 2. ብዛቱ አስር አስሮችን የሚያህል። *መቶ ሰዎች።*

መቶ በመቶ ሙሉ በሙሉ።

[የ] መቶ አለቃ ስ ከሻንበል በታች የሚገኝ ወታደራዊ ማእረግ።

***መቸ**

ምቹ ቅ 1. የሚደላ፥ ምቾት ያለው። 2. ተስማሚ የሆነ፥ የሰጠ። *ለካባቢው ትምህርት ቤት ለመስራት ምቹ ነው።*

ምቾት ስ ድሎት።

ተመቸ ግ 1. ደላ፥ ተስማማ። 2. ተባካ፥ ሆነ። *ከተመቸኝ እመጣለሁ።*

ተመቻቸ ግ 1. ተደላደለ፥ ተስተካከለ። 2. ተዘጋጀ፥ ተሰናዳ።

አመቸ ግ ምቹ፥ ተስማሚ ሆነ።

አመቺ ቅ ምቹ የሆነ፥ ተስማሚ።

አመቻቸ ግ 1. አደላደለ፥ አስተካከለ። 2. አዘጋጀ፥ አሰናዳ።

መቼ (መች) ተው.ግ. አንድ ጉዳይ የተከናወነበትን ወይም የሚከናወንበትን ጊዜ ለመጠየቅ የሚያገለግል የጥያቄ ቃል። *መቼ መጣህ?*

መቼም መች ምንጊዜም ቢሆን፥ በየትኛውም ጊዜ ቢሆን፥...። *መቼም መች እንደዚህ ሆኖ አያውቅም።*

መቼም(መቼውንም) ምንምጊዜ፥ አንድም ቀን። *መቼም እንደዚህ ዓይነት ነገር አጋጥሞኝ አያውቅም።*

ከመቼው ከምንጊዜው (ፍጥነትን ለማድነቅ የሚነገር)። *ከመቼው ሄደህ መጣህ?*

ከመቼውም ጊዜ ይልቅ/ይበልጥ/ያነሰ ከምንጊዜውም፥ ከማንኛውም ጊዜ ይልቅ ወይም ይበልጥ ወይም ያነሰ። *ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ዛሬ ተስማምቶኛል።*

መነመነ ግ 1. ቀጠነ፥ ኮሰመነ፥ ከሳ። 2. በጣም ትንሽ ሆነ፥ ጠበበ። *ተስፋው መነመነ።*

መንማና ቅ ከስማና።

ተመናመነ ግ ቀስ በቀስ እያለቀ ሄደ (ገንዘብ፥ እህል፥...)።

መነሳንስ "ነሰነሰ" ስር ተመ.

መነሸ ግ 1. በታተነ። *የተነጠፈውን አልጋ መነሸው።* 2. በቃንዱ መሬት እየጫረና እየቆፈረ አፈሩን ወደላይ ወረወረ (ውጊያ መግጠም ያማረውና ያሰኘው በሬ)።

መንሽ ስ በመውቃት ላይ ያለን እህል ለመበርበሪያ፥ ለመበተኛ፥ ለማዝሪያ፥... የሚያገለግል ከእንጨት የተሰራና ብዙውን ጊዜ ሶስት ጣት ያለው የአውድማ መሳሪያ።



መንሽ

ተመነሸ ግ አውድማ ላይ ያለ እህል በመንሽ ተበረበረ፥ ተበተነ።

አመነሸ ግ አውድማ ላይ እየተበራየ ያለን እህል በመንሽ ወደ ላይ በመወርወር በነፋስ አማካይነት ምርቱ ከገለባው እንዲለይ አደረገ።

***መነሸነሸ**

ምንሽንሽ ቅ ያጌጠ፥ ሽሙንሙን፥ የተዋበ።

ተምነሸነሸ ግ 1. ተሽሞንሞነ፥ አጌጠ። 2. (ገንዘብ ወይም ምግብ፥...) እንደልቡ በብዛት፥ አገኘ ወይም እንደፈለገው በብዛት ተጠቀመበት።

አምነሸነሸ ግ 1. አስጌጠ፥ አሽሞነሞነ። 2. አጠገበ፥ በብዛት ሰጠ ወይም ጋበዘ፥... (ምግብን፥ ገንዘብን፥...)።

መነሻ "*ነሳ" ስር ተመ.

መነሾ ዝ.ከ.

***መነቀ**

ምንቂያም ቅ (ስድብ) 1. ምንቅ ምንቅ የሚል። 2. ሴሰኛ።

ምንቅ ምንቅ አለ ግ ሲሄድ ወይም ሲራመድ ሰውነቱ ውዝ ውዝ፥ ውንጥ ውንጥ አለ።

መነቀለ ግ ከስሩ ነቀለ፥ መነገለ፥ መነቀረ።

መነቀረ ግ 1. መነገለ፥ መነቀለ። 2. በተነ፥ አፈረሰ፥ አቀማመጡን አበላሸ፥ መነጠረ።

መንቃራ ቅ (ስድብ) 1. ሰውነቱን እያቅበጠበጠና እያወዛወዘ የሚሄድ፥ ርጋታ የሌለው፥ ሲሄድ ወዲያና ወዲህ የሚረግጥ። 2. በሆነ ባልሆነው የቁጣ ስሜት የሚያሳይ፥ ቀልቃላ የሆነ፥ ርጋታ የሌለው።

ምንቅርቅሩ ወጣ በስርአት ተቀምጦ የነበረው ነገር ተበታተነ፥ ተበላሸ፥...።

ምንቅርቅራቸው ወጣ በከፍተኛ ደረጃ ተጣልተው ወይም ተናቁረው ተለያዩ።

ተመናቀረ ግ 1. ተጣላ፥ ተናቆረ። 2. በጥል ተለያየ። 3. ወዲያና ወዲህ ረገጠ፥ ተበራገደ። 4. ርጋታ በሌለው ሁኔታና በቁጣ ስሜት አንድ ድርጊት ፈፀመ (በንግግር፥ በስራ፥...)።

አመናቀረ ግ 1. አጣላ፥ አናቆረ። 2. በጥል አለያየ።

መነባንብ "ነበነበ" ስር ተመ.

መነተገ ግ መነተፈ፥ ቀማ፥ ነጠቀ።

መነተፈ ግ 1. ነጠቀ፥ ቀማ። 2. ሰረቀ።

መነቸከ ግ 1. በጣም አደፈ፥ ቆሸሸ። 2. በጣም ከማደፉ ወይም ከመቆሸሹ የተነሳ ቢያጥቡት አልፀዳ አለ (ለልብስ)። 3. አልታኘክ፥ አልገራ አለ፥ እኝ ሆነ (ስጋ)። 4. አላቆም ወይም አላባራ አለ (ዝናብ)።

መንቻካ ቅ 1. በቀላሉ የማይታኘክ፥ እኝ (ስጋ)። 2. ቶሎ የማያቆም ወይም የማያባራ (ዝናብ)። 3. (ዘይ.) ንዝናዛ፥ ጨቅጫቃ፥ ነገር ከያዘ የማይለቅ፥ ችኮ።

ተመናቸከ ግ ችክ አለ።

መነቸፈ ግ ነጨ፥ ቦጨቀ።

መነነ ግ የአለምን ነገር፥ ተድላና ደስታን ንቆና

ትቶ፡ ከሰው ተለይቶ በዱር፥ በጫካ ወይም በገዳም ሲኖር ሄደ።

መናኝ (መናኒ) ስ የመነነ መነኩሴ፤ ባህታዊ።

ምናኔ (ምነና) ስ (ሃይ.) የአለምን ነገር፥ ተድላ ደስታን ንቆና ትቶ ከሰው በመለየት በዱር፥ በጫካ ወይም በገዳም መኖር።

መነን ስ 1. ነጭና ቀጭን የሆነ የፈትል ዓይነት። 2. (ዘይ.) ሀ. ቆንጆ፥ ውብ (ለሴት)። ለ.በጣም ቀጭን የሆነና ውሃነት ያየለበት (ቡና፥ ጠላ፥...)

መነከሰ (መለከሰ) ግ መነኩሴ ሆነ።

መነኩሴ (መለኩሴ) (ብ.ቁ. **መነኮሳት**) ስ የምድራዊውን አለም ደስታና ድሎት በቃኝ ብሎ፥ ከፍትወተ ስጋ የተገለለና የተፀለየበት ወይም የተባረከ ቆብ የጫነ፤ ለነፍሱ ብቻ ያደረ ሰው (ለሴት መነኩሲት ይባላል)።

መነኩሲት ወፍ ስ እንደ ቆብ ያለ ቁንጮ ያላት ወፍ።

ምንኩስና ስ በአለም ላይ ያለውን ተድላና ደስታ ትቶና ንቆ በመገለል የመኖር ህይወት።

አመነኮሰ ግ ቀድሶ ባርኮና ተገቢውን ስርአተ ፀሎት አድርጎ ቆብ ጫነለት ፡ መነኩሴ አደረገ።

መነዘሰ ግ ሚዛን ደፋ፥ ከበደ፥ ወደ አንድ በኩል አጋደለ፥ አዘነበለ፤ አመዘነ።

መነዘረ ግ 1. ጥቅል ገንዘብን ተመጣጣኝ ዋጋ ወዳላቸው ቅንስናሽ ብሮች ወይም ሳንቲሞች ለወጠ፥ ዘረዘረ፥ ሸረፈ። 2. አንድን የሌላ አገር ገንዘብ ወደሌላ የውጭ አገር ገንዘብ ለወጠ፥ ቀየረ፤ ዘረዘረ። 3. ገንዘብ አወጣ፥ አባከነ፥ አጠፋ። *ገንዘቡን በሆነ ባልሆነው መንዝሮ ጨረሰው።* 4. ፀሃይ ወይም ነፋስ እንዲመታው ወይም እንዲያገኘው በተነ፥ ዘረጋ፥ አሰጣ፥ ዘረረ።

ምንዛሬ ስ 1. ከተወሰነ ጥቅል ገንዘብ ጋር እኩል ዋጋ የሚኖረው ቅንስናሽ ብር፥ ሳንቲም ወይም ዝርዝር ገንዘብ። 2. ለአንድ አገር ገንዘብ አቻ የሚሆን የሌላ አገር ገንዘብ።

ምንዝር ስ 1.በጥንታዊ የመሬት ስሪት ውስጥ በርስት አለቃው ስር ያሉና ዝምድና ያላቸው የርስቱ ተካፋዮች። 2. አለቃ ያልሆነ የበታች ሰራተኛ።

መነደበ ግ 1. ደበደበ፥ መታ፥ ነረተ (በዱላ፥ በብትር)። 2. ጎዳ፥ አሰቃየ (ችግር፥ ረሃብ)።

መነደገ ግ በሃይል ነጠቀ፤ መነጨቀ፥ ቀማ።

ተመነደገ ግ በፍጥነት አደገ፤ ረዘመ።

መነጀዘ ግ በጣም አደፈ፥ ቸከ።

መጅሊስ ስ ጉባኤ፥ ሸንጎ፤ ለተወሰነ አላማ አንድ ቦታ ላይ የተቀመጡ የሰዎች ስብስብ።

መነገለ ግ ከስሩ ነቀለ፥ ፈነቀለ።

መነገጃ "ነገደ" ስር ተመ.

መነገገ ግ መንገጭላ ወይም አገጭ ወይም ጉንጭ አካባቢ ይዞ አፍ አስከፈተ፤ ፈለቀቀ።

መንጋጋ በፊደል ተራው ተመ.

መነጎለ¹ ግ በሳ፤ ነደለ፥ ሰረሰረ።

መንጎል ስ ጠፍርን፥ ቀበቶን፡... ለመብሳት የሚያገለግል እንደ ወስፌ ያለ መሳሪያ።

መነጎለ² ግ ተናፈጠ፤ ጎልጉሎ አወጣ (ንፍጥን)።

መንጎል ስ ተጎልጉሎ የወጣ ወፍራም ንፍጥ።

መነጠ ግ በጣም ደሀየ፤ ተቸገረ።

መናጢ ቅ 1. ምንም የሌለው፤ ድሃ፥ ምስኪን። 2. ክፉ።

መነጠረ ግ 1. ጫካ፥ ዱር፥ ሳር ያለበትን ቦታ በመጨፍጨፍ ወይም በማጨድ አፀዳ፤ ወለል አደረገ። 2.ለይቶ አወጣ፤ አጠፋ። *ህዝቡ ሌቦችን ከያሉበት መነጠረ።* 3. በደንብ፥ ጥርት አድርጎ አጠበ። 4. በአርጩሜ ወይም በአለንጋ ገረፈ።

መነጠቀ ግ 1. በድንገት በሃይል ቀማ፤ ነጠቀ፤ መነጨቀ። 2. ነቅሎ፥ ስቦ፥ መዝዞ፥ ጎትቶ አወጣ። 3. ደምን በዋገምት ሳበ፤ ነጠቀ።

መንጠቆ ስ ሹልና ቆላፋ የሆነ የአሳ መያዣ ወይም ማጥመጃ ብረት።

ተመነጠቀ ግ 1.ድንገት ብድግ ብሎ ሄደ። 2 መጠቀ፤ ራቀ፤ ከፍ አለ ። 3. ፈጣን እድገት አሳየ።

መንጥር "መንፀር" ን ተመ.

መነጨ ግ 1. ፈለቀ፥ ተንፎለፎለ፥ ፈሰሰ፥ ጎረፈ (ለምሳሌ ውሃ ከመሬት ውስጥ)። 2. ተገኘ፤ ፈለቀ (ሃሳብ)።

ምንጭ ስ 1. ከመሬት ውስጥ ውሃ በተፈጥሮ የፈለቀበት ቦታ። 2. የአንድ ነገር መገኛ፥ መነሻ፥ ምክንያት።

አመነጨ ግ 1. ውሃ አፈለቀ። 2. አፈሰሰ፥ አወረደ (እንባን)። 3. አገኘ፥ አመጣ፤ አፈለቀ (ሃሳብን፥ መፍትሄን፤...)።

መነጨረ ግ 1. በተነ፤ ጫረ። 2. ጠጉርን በሚዶ አበጠረ።

መንጫራ ቅ 1. ፀጉሩ የተንጨበረረ። 2. (ዘይ.) ቁጡ፤ ጠባዩ የማይመች።

መነጨቀ ግ በሃይል በድንገት ነጠቀ፤ ወሰደ።

***መነጨቀ**

መንጫቃ ቅ ነዝናዛ፥ ጨቅጫቃ።

ተመናጨቀ ግ ተቆጣ፥ ተቆናጠረ።

አመናጨቀ ግ በቁጣና በማጥሳሳት ወይም

በንቀትና ስነስርአት በጎደለው አኳኋን ተናገረ።

መነፅር (መነጥር) ስ ክብ ወይም ሞላላ ወይም አራት ማእዘን ቅርፅ ያላቸው ጥንድ የማሳያ ብርጭቆዎች የተገጠመለት፥ ጆሮዎች ላይ የሚያርፉ ሁለት ዘንግ ያሉትና አፍንጫ ላይ እንዲያርፍ ሆኖ የተሰራ፥ በተለያዩ የአይን በሽታ ምክንያቶች የማየት አቅም ሲደክም ወይም አይንን ከፀሃይ ብርሃን ለመከላከል ሲባል አይን ላይ የሚደረግ መሳሪያ፥ አይነርግብ።

መነፅር

መነፍ "**ነፈፈ**" ስር ተመ.

መና 1. ከንቱ፥ ብላሽ፥ ዋጋ የሌለው። 2. ባዶ። *ገንዘቡን ሳያገኝ መናውን ቀረ።*

መና ቀረ 1. ባዶውን ቀረ። 2. ከንቱ፥ ብላሽ ሆኖ ቀረ።

መኗ ስ በመፅሃፍ ቅዱስ እንደተፃፈው እግዚአብሄር ከሰማይ እያወረደላቸው እስራኤላውያን በምድረ በዳ ሳሉ ይመገቡት የነበረ ምግብ።

መናህሪያ ስ 1. የህዝብ ማጓጓዣዎች (መኪና፥ ባቡር፥...) መነሻና መድረሻ ጣቢያ። 2. መገናኛ፥ መሰብሰቢያ፥ መከማቻ። *የነጋዴዎች መናህሪያ* /የሌቦች መናህሪያ።

መናሄ "**ምናሄ**"ን ተመ.

መናኛ ቅ ጥራት የሌለው፥ ተራ።

መናኝ "**መነነ**" ስር ተመ.

መናጆ "**ነዳ**" ስር ተመ.

መናገሻ ከተማ "**ነገሰ**" ስር ተመ.

መናጢ "**መነጠ**" ስር ተመ.

መናፈሻ "**ነፈሰ**" ስር ተመ.

መናፍቅ ስ በአንድ ሃይማኖት ውስጥ አጠቃላይ ከሆነው ከእምነቱ ድንጋጌ ውጪ ለየት ያለ መንገድ ይዞ የሚከተልና በእምነቱ ውስጥ ያሉትን አንዳንድ መሰረታዊ ነጥቦች የማይቀበል፤ ተጠራጣሪ።

መን ስ ሸማኔ የግራና የቀኝ እግሩን እያፈራረቀ ሲረግጠው እንዱ ወደ ላይ ሌላው ወደታች በመሆን ድርና ማግን የሚያስባጥር ወይም የሚያመሳስብ የሸማኔ እቃ።

መንማና "**መነመነ**" ስር ተመ.

መንስኤ "***ነሳ**" ስር ተመ.

መንሸላሊት "**እንሽላሊት**"ን ተመ.

መንሽ "**መነሸ**" ስር ተመ.

መንቀል ስ ረዘም ብሎ ቀጠን ያለ አንገት ያለው የውሃ መያዣ ቅል ወይም ሸክላ።

መንቀል

መንቀሻ¹ "**ነቀሰ¹**"ስር ተመ.

መንቀሻ² "**ነቀሰ²**" ስር ተመ.

መንቃራ "**መነቀረ**" ስር ተመ.

መንቆር "**ነቆረ**" ስር ተመ.

መንበር ስ 1. መቀመጫ ወይም ወንበር (ለንጉስ፥ ለፓትርያርክ፥...)። 2. እንደ ቁም ሳጥን ሆኖ በአራት ማእዘን መልክ የተሰራ የታቦት ወይም የፅላት ማስቀመጫ።

መንበረ መንግስት ስ የንጉስ የክብር መቀመጫ ወይም ወንበር፥ ዙፋን።

መንበረ ፀባእት ስ ሰማያዊ የአምላክ ዙፋን።

መንታ ስ 1. በአንድ ጊዜ ከአንዲት እናት የተወለዱ ቁጥራቸው ከአንድ በላይ የሆኑ ልጆች፥ ግልገሎች፥...። ቅ 2. የታችኛው ክፍሉ አንድ ሆኖ ከላይ እንደ ባላ ሁለት የሆነ።

መንታ መንገድ ስ ከተለያዩ አቅጣጫዎች የሚመጡ መንገዶች የሚገናኙበት ወይም አንድ መስመር የነበረው ወደ ተለያዩ አቅጣጫዎች የሚከፋፈልበት መንገድ።

መንታ ምላስ 1. ለፍላፊ፥ ተሳዳቢ። 2. አንድን ጉዳይ በሚመለከት አንድ ጊዜ ሌላ፥ ሌላ ጊዜ ደግሞ ከበፊቱ የተለየ ሌላ ነገር የሚናገር፥ ቀላማጅ።

መንትያ ስ ከአንድ እናት ባንድ ጊዜ ከተወለዱት መንታ ልጆች አንዱ።

መንቻካ "**መነቸከ**" ስር ተመ.

መንከላወሻ "**ከለወሰ**" ስር ተመ.

መንከት "**ነከተ**" ስር ተመ.

መንከፍ ቅ ቂል፥ ሞኝ፥ እንከፍ።

መንካ ቁልቋል የ"**ቁልቋል**"ን 1ኛ ፍቺ ተመ.

መንካከ ስ የበቆሎ ቅንጨ።

መንኮራኩር ስ ከመሬት ውጭ ወደ ላሉ

ፕላኔቶች ወይም በጠፈር ላይ ለሚከሄዱ ልዩ ልዩ ጥናቶች የሚላኩ ተመራማሪዎች፥ መሳሪያዎች+... የሚጓጓዙበት ዘመናዊ መሳሪያ።

መንደልት "ነደለ" ስር ተመ.

መንደልቶ ዝ.ከ.

መንደሪን ስ እንደ ብርቱካን ያለ፥ ቅርፊቱ በቀላሉ ሊላጥ የሚችልና ውስጡ ብዙ ፍሬዎች ያሉት የሚበላ የፍራፍሬ አይነት፡፡

መንደር ስ በተወሰነ አካባቢ ቤቶች እጅብ ብለው፥ ተቀራርበው የተሰሩበት፥ በገጠር ወይም በከተማ ውስጥ የሚገኝ የመኖሪያ ቦታ፤ ሰፈር፤ አምባ።

መንደረኛ ቅ መንደር ለመንደር የሚዞር፥ ስራ ፈት፥ አውደልዳይ።

መንደርተኛ (መንደረተኛ) ስ በአንድ መንደር የሚኖሩ ሰዎች።

መንደርቶ ስ ራሳም ወይም ቋራም ዱላ፤ መንዶ።

መንደርደሪያ "ደረደረ" ስር ተመ.

መንዲስ ቅ ወፍራም፥ ደንዳና፥ ግዙፍ።

መንዶ (ሜንዶ) ስ መንደርቶ።



መንዶ

መንጃ ፈቃድ "ነዳ" ስር ተመ.

መንገድ ስ 1. መሄጃ፡ መተላለፊያ፡ መመላለሻ፣ ጎዳና። 2. ዘዴ፥ ብልሃት፥ አሰራር። *ችግሩን በሌላ መንገድ ማስወገድ ይቻላል።* 3. አቅጣጫ፥ መልክ፥ በኩል። *ጉዳዩን በሁለት መንገድ ማየት ይቻላል።*

መንገድ ሄደ ራቅ ወዳለ ቦታ ሄደ።

መንገድ ለቀቀ አሳለፈ፥ መተላለፊያ ሰጠ፤ ዞር አለ።

መንገድ መታው ብዙ መንገድ በመሄዱ ደከመ፤ ጣመነ።

መንገድ ሰጠ 1. አሳለፈ፥ ዞር አለ፥ መንገድ ለቀቀ። 2. አንድ ነገር እንዲያደርግ አሳየ፤ መራ።

መንገድ ቀደደ 1. መንገድ አወጣ፥ አበጀ። 2. አዲስ ስራን ለመስራት የመጀመሪያው ሰው ሆነ።

መንገድ አወጣ በፊት ያልነበረ አዲስ መንገድ ወይም መተላለፊያ ሰራ፤ መንገድ ቀደደ።

መንገድ አገኘ 1. ሰበብ፥ ምክንያት አገኘ። 2. ዘዴ፥ ብልሃት አገኘ።

መንገድ ከፈተ 1 አዲስ መንገድ፥ ጎዳና ሰራ፤ መንገድ ቀደደ። 2 አሳለፈ፥ ዞር አለ፥ መንገድ ለቀቀ። 3. አዲስ ስራን ለመስራት የመጀመሪያው ሰው ሆነ።

መንገድ ያዘ ፈር፥ መስመር ያዘ።

መንገድ ጠረገ መንገድ ቀደደ።

መንገድ ጠራጊ አንድ አዲስ ስራን ለመስራት የመጀመሪያ የሆነ፥ ጀማሪ።

የመንገድ አልጋ ስ መጠኑ አነስተኛ የሆነና መተጣጠፍ የሚችል፣ ለማጓጓዝ አመቺ የሆነ አልጋ።

መንገደኛ ስ 1. በመንገድ ላይ የሚተላለፍ፤ አላፊ አግዳሚ። 2. ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለመሄድ ወይም ለመጓዝ የተነሳ ወይም በመጓዝ ላይ ያለ። 3. አንድ ቦታ ረግቶ የማይቀመጥና መንገድ የሚያበዛ ሂያጅ።

መንገጭላ (መንጋጭላ) ስ የታችኛዎቹ ጥርሶች የሰፈሩበት አካል፤ አገጭ፥ ግንጭል።

መንጋ ስ 1. በአንድነት የተሰበሰበ ከብት። 2. ብዙ፤ አያሌ። *መንጋ ፈረ።*

መንጋጋ ስ የውሻ ክራንቻ ከሚባለው ጥርስ ሂላ የሚገኝና ምግብ ለማኘክና ለማድቀቅ የሚያገለግል ጠፍጠፍ ያለ ትልቅ ጥርስ።(ስእሉን ጥርስ ስር ተመ.)።

መንጋጭላ "መንገጭላ"ን ተመ.

መንግስት "ነገሰ" ስር ተመ.

መንኅል^{1} "መነኅለ^{1}" ስር ተመ.

መንኅል^{2} "መነኅለ^{2} ስር ተመ.

መንኅል^{3} ስ ቀለም እየተጠቀሰ የሚፃፍበት ብእር የተሰካበት ዘንግ፤ የብእር እጀታ።

መንጠቆ "መነጠቀ" ስር ተመ.

መንጫራ "መነጨረ" ስር ተመ.

መንጫቃ "መነጨቀ" ስር ተመ.

መንጮረር "ጮረረ" ስር ተመ.

መንፈስ (ብ.ቁ. **መናፍስት**) ስ 1. የማይዳሰስ፥ የማይጨበጥ፥ ረቂቅ ነገር። 2. ህሊና፥ አእምሮ። *የመንፈስ ደስታ አገኘ።* 3. ስሜት፥ ፍላጎት። *መንፈሱ ተነሳሳቷል።* 4. የነገር፥ የስራ፥ የሃሳብ አዝማሚያ፥ ሁኔታ።

መንፈሱ ሞተ ተስፋ ቆረጠ፥ የመንፈስ ብርታት አጣ።

መናፍስት ስ 1. የመንፈስ ብዙ ቁጥር። 2. አጋንንት።

መንፈሰ ደካማ ስ ወኔ ቢስ፡ ሃሞተ ቢስ፡

በቀላሉ ተስፋ የሚቆርጥ።

መንፈስ ጉባኤ (መንፈሳዊ ጉባኤ) ስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በመንፈሳዊ ተግባር ረገድ ልትፈፅመውና ልትከተለው የሚገባትን ጉዳይ እየመከረ እንዲወስን በ1918 ዓ/ም የተቋቋመ ጉባኤ።

መንፈሰ ጠንካራ ስ ተስፋ የማይቆርጥ፣ የማይበገር፣ ብርቱ፣ ፅኑ።

መንፈስ ቅዱስ ስ 1.የእግዚአብሄር ባህርይ የሆነ፣ የማይዳሰስና የማይጨበጥ ረቂቅ መለኮታዊ ሃይል። 2. ከሶስቱ ስላሴዎች አንዱ የሆነ እግዚአብሄር አምላክ።

መንፈሳዊ ቅ 1. ሃይማኖት ነክ። 2. ሃይማኖተኛ፣ አማኝ፣ የእግዚአብሄርን ትእዛዝ የሚያከብር። 3. በሃይማኖቱ ስርአት መሰረት ከሞት በሁዋላ ላለው ህይወት ራሱን የሚያዘጋጅ፤ አለማዊ ያልሆነ።

መንፈሳዊ ቅናት ስ ሌላው ከደረሰበት ደረጃ ለመድረስ፣ ያደረገውን ጥሩ ነገር ለማድረግ፣... የሚፈጠር በምቀኝነት ላይ ያልተመሰረተ የፉክክር ስሜት፣ ፍላጎት።

መንፈሳዊ ባህል ስ እንደ ሙዚቃ፣ ስነፅሁፍ፣ ስእል፣ ርእዮተኣለም፣ ስነ ምግባር፣... ያለ የአንድ ማህበረሰብ ባህል።

መንፈሳዊ ትምህርት ስ ሃይማኖት ነክ ትምህርት።

መንፈቅ ስ የስድስት ወር ጊዜ ወይም የአመት አጋማሽ።

መንፈቀ ሌሊት ስ እኩለ ሌሊት።

መንፈቀ መአልት ስ እኩለ ቀን።

መኖ ስ የከብት ቀለብ።

መኖሪያ "ኖረ" ስር ተመ.

__*መኘ__

ምኞት ስ አንድን ነገር የማድረግ፣ የማግኘት፣... ፍላጎት፣ ጉጉት፣ ክጀላ።

ተመኘ ግ አንድን ነገር ለማግኘት፣ ለማድረግ፣... ፈለገ፣ ከጀለ፣ ጓጓ።

መኝታ "ተኛ" ስር ተመ.

መአልት ስ ከጠዋት እስከ ማታ ያለው የብርሃን ጊዜ፣ ቀን።

መአት ስ 1. ከፍተኛ እልቂት፣ ችግር፣... የሚያስከትሉ እንደ ረሃብ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ፣ ቃጠሎ፣... የመሳሰሉ አደጋ፤ መቅሰፍት። 2. (ዘይ.) በጣም ብዙ፣ አያሌ። *መአት ጓደኞች አሉት።*

መአት አወራ የመከራ፣ የችግር፣... ወሬ አጋኖ ነገረ፣ ተናገረ።

መአት አውሪ ሁልጊዜ የመከራን፣ የችግርን፣... መምጣት ብቻ የሚናገር።

መአተኛ ቅ 1. ብዙ ጊዜ ስለጭንቅ፣ ስለመከራ፣ ስለችግር፣... አጋኖ የሚያወራ። 2. የሚሰራው ሁሉ የሚያስደንቅ፤ የሚያስገርም፤ ተአምረኛ።

መአዛ (ማዛ) ስ ደስ የሚል ሽታ ወይም ጠረን።

መከለሻ "ከለሰ" ስር ተመ.

መከላ (መከሉ) ስ ጓል፣ ፍንቃይ።

መከላከያ "ከለከለ" ስር ተመ.

መከመከ ግ ላላ፣ ለሰለሰ፣ ትምክ ትምክ አለ።

መከረ ግ 1. እንዲህ ቢሆን ይሻላል ብሎ ለሌላ ሰው ነገረ፣ ሃሳብ ሰጠ። *ለክረምቱ የዝናብ ልብስ እንድገዛ መከረኝ።* 2. አስጠነቀቀ፣ ገሰፀ። *ዳግመኛ አልኮል እንዳይጠጣ መከረው።* 3. ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ሰው ባንድነት ዶለተ፣ አሴረ። 4. ተወያየ፣ ሃሳብ ለሃሳብ ተለዋወጠ። *ከመምህራኖቻቸው በራት በጉዳዩ ላይ ብዙ መክረውበታል።*

መማክርት ስ የምክር ቤት አባላት።

መካሪ ቅ 1. ምክር የሚሰጥ። 2. ተቆጪ፣ የሚገስፅ።

መክር ዝ.ክ.

ምክር ስ 1. ይጠቅማል ተብሎ የሚቀርብ ሃሳብ፣ አስተያየት፣...። 2. መደረግ ያለበትንና የሌለበትን ለመምረጥ በሰዎች መካከል የሚደረግ ውይይት፣ ንግግር፣ የሃሳብ ልውውጥ። 3. ተግሳፅ፣ ማስጠንቀቂያ። *ይህ ልጅ ፀባዩ የተበላሸ ነው ምክር ያስፈልገዋል።*

ምክር ሰማ የተባለውን፣ የተነገረውን ተቀበለ፣ ፈፀመ፣ በስራ ላይ አዋለ።

ምክር ተቀበለ ዝ.ክ.

ምክር ቤት ስ 1. የተወሰኑ ሰዎች በአባልነት ተመርጠው ወይም በሙያቸው ተቀጥረው አንድ የተወሰነ ስራ የሚያከናውኑበትና ድርጅቱ ወይም ቢሮው የተቋቋመበትን አላማ መሰረት በማድረግ ልዩ ልዩ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ውሳኔዎች የሚያስተላልፉበት ቢሮ ወይም ድርጅት፤ የሰዎቹ ስብስብም ምክር ቤት ይባላል። ምሳሌ ህግ መወሰኛ ምክር ቤት /ንግድ ምክር ቤት። 2. ፓርላማ።

ምክክር ስ መደረግ ያለበትንና የሌለበትን ለመወሰን ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች መሃከል የሚካሄድ ውይይት፣ የሃሳብ ልውውጥ።

ተመከረ ግ 1. ምክር ሰማ፣ ተቀበለ። 2. በአንድ ጉዳይ ላይ ውይይት፣ ምክር ተደረገ።

ተመክሮ ስ ምክር። *ተፈጥሮን ተመክሮ አይመልሰውም።*

ተመካከረ ግ ሃሳብ ለሃሳብ ተለዋወጠ፣

ተወያየ።

ተማከረ ግ አንድን ጉዳይ ለማድረግ ወይም ላለማድረግ የሌላ ሰውን ሃሳብ፣ አስተያየት ጠየቀ፤ ከሌላ ሰው ጋር ተነጋገረ።

አመክሮ ስ ምክር፣ ተግሳፅ፣ ማስጠንቀቂያ። *እስረኞቹ በአመክሮ ተፈቱ።*

አማከረ ግ 1. ምክር፣ ሃሳብ፣ አስተያየት ጠየቀ፤ እንዴት ቢሆን ይሻላል አለ። 2. በምክር ረዳ፣ አገዘ፣ ሃሳብ፣ አስተያየት ሰጠ።

አማካሪ ቅ 1.አንድን ስራ፣ ጉዳይ፣... በተመለከተ የሙያ ምክር የሚሰጥ ባለሙያ። *የህግ አማካሪ* ስ 2.ሃሳብ፣ አስተያየት፣ ምክር የሚሰጥ።

መከራ ስ ፈተና፣ ጭንቅ፣ ስቃይ።

መከራ ቀመሰ ችግር፣ ስቃይ ደረሰበት።

መከራ በላ ተሰቃየ፣ ተቸገረ።

መከራ ዛቀ ብዙ መከራ ደረሰበት።

መከራውን አየ 1. ለፋ፣ ማሰነ። 2. ተቸገረ፣ ተሰቃየ።

መከረኛ ቅ ችግር፣ ስቃይ፣ መከራ የማይለየው።

መከር (መህር) ስ በክረምት ተዘርቶና በቅሎ የደረሰው እህል የሚታጨድበትና የሚሰበሰብበት ወቅት።

መከር ተከተተ በመከር ወቅት የተገኘው ሰብል ታጭዶ፣ ተሰብስቦና ተወቅቶ ወደ ጎተራ ገባ።

መከተ ግ 1. ተከላከለ (ጦርን በጋሻ፣ ዱላን በዱላ ወይም በእጅ፣...)። 2. አገደ፣ መለሰ፣ ተቋቋመ። 3. ጋረደ፣ ከለለ፣ ሸፈነ፣ መከታ ሰራ።

አይመክተውም1.አይመልሰውም 2. አይበቃውም፣ አያጠግበውም።

መከታ ስ 1.መከላከያ ወይም መመከቻ ጋሻ። 2. በሸንበቆ፣ በጨፈቃ፣... የሚሰራ ከለላ፣ ግርዶሽ።

ምክቶሽ (ምክት) ስ ሁለት ሰዎች አንዱ ሌላውን በያዘው ዱላ እንዳይመታው እየተከላከሉ የሚጫወቱት ባህላዊ ጨዋታ።

መክተቻ "ከተተ" ስር ተመ.

መከነ ግ 1. የማይወልድ፣ ፍሬ የማይሰጥ ሆነ። 2. ጠፋ፣ ሞተ (ሆድ ውስጥ ያለ የኮሶ ትል)።

መካን (መሃን) ስ መውለድ የማትችል ሴት ወይም ማስወለድ የማይችል ወንድ።

መካን እንዶድ ስ የማያፈራ እንዶድ።

የመሃን ልጅ ብርቅዬ፣ የሚሳሱለትና ተሞላቆ ያደገ ልጅ።

***መከኘ**

ምክንያት ስ 1. አንድ ነገር ሊሆን፣ ሊፈፀም፣ ሊደረግ የቻለበት ወይም የሚችልበት መሰረተ ነገር፤ ሳቢያ፤ መንሾ። 2. ሰበብ። *ላለመስራት ምክንያት አታብዛ።*

ተመካኘ ግ 1. በሌላ ተሳበበ፣ ተሳከከ። 2. ሰበብ፣ ምክንያት ተሰጠ።

አመካኘ (አመሃኘ) ግ 1. በሌላ አሳበበ፣ አሳከከ። 2. ሰበብ፣ ምክንያት ሰጠ።

መከዳ ስ እንደ ትራስ ሆኖ የተሰራ የእጅ፣ የጎን መደገፊያ።

መክፍክፊያ "ከፈከፈ" ስር ተመ.

መኪና ስ ሰውን፣ እቃን፣... በመሬት ላይ ለማጓጓዝ የሚያገለግል አራት ወይም ከዚያ በላይ ጎማዎች ሊኖሩት የሚችልና ሞተሩ በነዳጅ ሃይል የሚንቀሳቀስ የተሽከርካሪ አይነት (ስእሉን መጓጓዣ ስር ተመ.)።

መኪና ያዘ የሚነዳው መኪና አገኘ ወይም ባለመኪና ሆነ።

መኪና ሰፊ ስ ልብስ ሰፊ።

መኪና ነጂ ስ ሾፌር።

***መክ**

ተመካ ግ ተማመነ (በሃብቱ፣ በእውቀቱ፣ በወገኑ፣...)።

መመኪያ ስ አለኝታ፣ መከታ፣ መኩሪያ።

ትምክህት ስ ከመጠን በላይ በራስ መመካት፣ መተማመን፤ ራስን ከፍ አድርጎ የማየት ስሜት።

ትምክህተኛ ቅ ከመጠን በላይ በራሱ የሚመካ፣ የሚተማመን፣ ራሱን ከፍ አድርጎ የሚያይ፣ ማንአህሎኝ ባይ።

አስመካ ግ አኮራ። *የሚያስመካ ስራ ሰርቷል።*

መካሪ "መከረ" ስር ተመ.

መካር ዝ.ከ.

መካተቻ "ከተተ" ስር ተመ.

መካኒክ (ሜካኒክ) ስ ሞተር ነክ የሆኑ ነገሮችን፣ ማሽኖችን፣ መኪናን፣... የማደስ፣ የመገጣጠም፣... ስራ የሚሰራ ባለሙያ።

መካን "መከነ" ስር ተመ.

መካከለኛ "*ማከለ" ስር ተመ.

መካከል ዝ.ከ.

መካያ ስ መጨረሻ።

በመካያው በስተመጨረሻ፣ በሗላ። *በመካያው ነገሩ ሁሉ እንዲህ ሆነ!*

መኬ ስ ዥንጉርጉር መልክ ያለው አደንጓሬ።

መክሊት ስ ሰላሳ ኪሎ ግራም ያህል የሚመዝን የክብደት መለኪያ።

መክሰስ ስ በምሳና በእራት መካከል ለእራት

መጸረሻ ተብሎ የሚበላ ምግብ፤ መቆያ።

መክተፊያ "ከተፈ" ስር ተመ.

መክደኛ "ከደነ" ስር ተመ.

መክድ ስ የጎራዴ እጀታ።

መክፈልት "*ከፈለ" ስር ተመ.

መክፈቻ "ከፈተ" ስር ተመ.

መክፈያ "ከፈለ" ስር ተመ.

መኮሮኒ (**ማኮሮኒ**) ስ ከስንዴ ዱቄት ሊጥ በተለያየ ቅርፅ (ውስጠ ክፍት፣ ጥምዝ፣...) ሆኖ ባጫጭሩ የሚዘጋጅና ተቀቅሎ የሚበላ የምግብ አይነት።

መኮስተሪያ "ኮስተረ^1" ስር ተመ.

መኮትኮቻ "ኮተኮተ" ስር ተመ.

መኮንን ስ 1. በወታደራዊ ስርአት ከምክትል መቶ አለቃ በላይ ያለ ማእረግ ያለው ሰው። 2. የአንድ ስራ ወይም ጉዳይ የበላይ፣ ሃላፊ፣ አዛዥ (በወታደራዊ ስርአት)። *የዘመቻ መኮንን።*

መኳንንት (ነጠ.ቁ. **መኮንን**) ስ በንጉሳዊው ስርአት ውስጥ ለዙፋኑ ቅርበት ያላቸውና ልዩ ልዩ ማእረግ የሚሰጣቸው ሰዎች ።

መወልወያ "ወለወለ" ስር ተመ.

መወርወሪያ "ወረወረ" ስር ተመ.

መወድስ "ወደሰ" ስር ተመ.

መወጠሪያ "ወጠረ" ስር ተመ.

መወጣጫ "ወጣ" ስር ተመ.

መዋሰእት ስ ቅዱስ ያሬድ የደረሰው የዜማ መፅሃፍ ስም፤ በአላትን፣ በይበልጥም ደግሞ ሙታንን አስመልክቶ በዜማ የሚባል ምስጋና፣ ፀሎት።

መዋቅር "ወቀረ" ስር ተመ.

መዋያ "ዋለ" ስር ተመ.

መዋጀ ስ ቀንበር የሚያርፍበት የበሬ ጫንቃ እንዳይጎዳ ሲባል በቀንበሩ ግራና ቀኝ ላይ የሚደረግ ቆዳ።

መዋጥ ስ ኬሻን፣ ጆንያን፣ ፍራሽንና የመሳሰሉትን ለመስፋት የሚያገለግል በመርፌ ቅርፅ የተሰራ ረዘምና ወፈር ያለ መስፊያ።

መዋጮ "ወጣ" ስር ተመ.

መውረጃ "ወረደ" ስር ተመ.

መውቀጫ "ወቀጠ" ስር ተመ.

መውዜር ስ የጠመንጃ አይነት።

መውደቂያ "ወደቀ" ስር ተመ.

መውጅ ስ ማእበል፣ ሞገድ።

መውጫ "ወጣ" ስር ተመ.

መዘለሻ "ዘለሰ" ስር ተመ.

መዘለግ "ለመዘገ" ን ተመ.

መዘለፊያ "ዘለፈ^2" ስር ተመ.

መዘመዘ ግ 1. ቆጠቆጠ፣ ጠዘጠዘ፣ መጠመጠ (ቁስል)። 2. ሰቦ፣ መጥጠ አወጣ። *ልብሱን በበረኪና ዘፍዝፈህ ላቆየው፣ ቆሻሻውን በደንብ እንዲመዘምዘው።*

መዝሙር "ዘመረ" ስር ተመ.

መዘራዝር "ዘረዘረ" ስር ተመ.

መዘርዝር ዝ.ክ.

መዘበረ ግ 1. አፈረሰ፣ ናደ፣ ገለባበጠ፣ አጠፋ፣ አወደመ። 2. ዘረፈ፣ በዘበዘ፣ ባዶ አስቀረ።

ምዝበራ ስ ዝርፊያ፣ ብዝበዛ።

ምዝብር ቅ የተበዘበዘ፣ የተዘረፈ። *ምዝብሩ ህዝብ፣...።*

ተመዘበረ ግ ተበዘበዘ፣ ተዘረፈ።

መዘበቻ "ዘበተ" ስር ተመ.

መዘባበቻ ዝ.ክ.

መዘነ ግ 1. ለካ፣ ሰፈረ፣ መጠነ (ክብደትን)። 2. ከሌላው ይበልጥ ከበደ፣ ወደ አንድ ወገን አጋደለ። *ከአንድ ጆንያ ጥጥ አንድ ጆንያ ጨው ይመዝናል።* 3. ገመተ፣ ገመገመ። *የነገሩን አካሄድ መዝኖ የራሱን ውሳኔ ይሰጣል።*

ሚዛን ስ 1. የክብደት መለኪያ። 2. የአንድ ነገር ክብደትን ለመለካት የሚያገለግል መሳሪያ።

ሚዛን 2ኛ ፍቺ

ሚዛኑን ጠበቀ ሳይወድቅ ወይም ሳይንገዳገድ ለመሄድ፣ ለመቆም፣ ለመቀመጥ፣... ተስተካከለ፣ ተደላደለ።

የሚዛን ልሳን ስ ክብደቱ ወደበለጠበት የሚደፋ ወይም ወደቀለለበት የሚያቀና የሚዛኑ ልክ ማወቂያ ምልክት፣ ላንሲታ።

የሚዛን ውልብልቢት ስ የሚዛን ልሳን።

ተመዘነ ግ ተለካ፣ ተሰፈረ፣ ክብደቱ ታወቀ።

አመዘነ ግ 1. ወደ አንድ በኩል አጋደለ፣ ከበደ፣ አዘነበለ። 2. አደላ። *ልቡ ወደ እሷ ያመዝናል።* 3. በለጠ፣ ከፍ አለ። *ከጉዳቱ ጥቅሙ ያመዝናል።*

በአመዛኙ በይበልጥ።

አመዛዘነ ግ 1. አሰበ፣ አወጣ አወረደ፣ አሰላሰለ። 2. አስተያየ፣ አነፃፀረ፣ አወዳደረ።

አመዛዛኝ ቅ የሚያስተውል፣ የሚያስብ።

አስመዘነ ግ በሚዛን አስለካ፣ ክብደቱ እንዲታወቅ አደረገ።

መዘክሪያ "ዘከረ" ስር ተመ.

መዘክር ዝ.ከ.

መዘወሪያ "ዘወረ" ስር ተመ.

መዘውር ዝ.ከ.

መዘዘ ግ ስበ፣ ለይቶ፣ ጎትቶ አወጣ።

መዝዞ አወጣ ካለበት፣ ከተደበቀበት ፈልጎ አወጣ፣ አጋለጠ፣ አሳየ።

መዘዝ ስ 1.የጠብ፣ የነገር፣ የክፉ አጋጣሚ፣... መነሻ ምክንያት፣ ጠብ፣ ሰበብ። 2. በአንድ ነገር ምክንያት ተያይዞ የሚመጣ ችግር።

መዘዘኛ ቅ ጠበኛ፣ ጠንቀኛ፣ ሰበበኛ።

መዘዝ ስ መለሎ፣ ቁመቱ ዘለግ ያለ፣ ሎጋ።

ተመዘዘ ግ አደገ፣ ረዘመ፣ ቁመት ጨመረ።

ተማዘዘ ግ ከተጣላው ሰው ጋር ለመታኮስ፣ ለመፋለም፣ ለመጋደል፣... ዱላ ወይም ሌላ መሳሪያ አወጣ። *ከባላጋራው ጋር ሽጉጥ ተማዘዙ።*

አማዘዘ ግ ሰዎች በዱላ ወይም በሌላ መሳሪያ ለመፋለም እንዲጋበዙ ሰበብ፣ ምክንያት፣...ሆነ፣ አጣላ።

መዘገበ ግ 1. በመረጃነት እንዲያገለግል ፃፈ፣ በሰነድ አሰፈረ (አንድን የተወሰነ ጉዳይ)። 2. በአንድ ቡድን ወይም ተቋም ውስጥ አባል አድርጎ ያዘ ወይም ስሙን ፃፈ።

መዝገብ ስ ልዩ ልዩ መረጃዎች (የስም፣ ወይም የሰነድ ዝርዝር ወይም ወጪና ገቢ) ተመዝግበው የሚያዙበት ትልቅ ደብተር።

መዝገበ ቃላት ስ በአንድ ቋንቋ ውስጥ የሚገኙ ቃላት በፊደል ተራቸው ተመዝግበውና በራሱ ወይም በሌላ ቋንቋ ፍቺ ተሰጥቷቸው የሚገኙበት መፅሀፍ።

መዝገብ ቤት ስ አንድ መስሪያ ቤት የሚያከናውናቸው ጉዳዮችና የመስሪያ ቤቱን ሰራተኞች የሚመለከት መረጃ ተመዝግቦ የሚቀመጥበት ክፍል።

ምዝገባ ስ ለአንድ ለተወሰነ ተግባር ስምን የመፃፍ ወይም የማፃፍ ተግባር።

ተመዘገበ ግ (አንድ መረጃ፣ ስም ዝርዝር፣...) በፅሁፍ ሰፈረ፣ ተፃፈ፣ ተያዘ።

አስመዘገበ ግ አንድ ከፍተኛ ውጤት በማምጣት ወይም ከፍተኛ ተግባር በማከናወን ራሱን አሳወቀ፣ የበላይነቱን አሳየ።

***መዘገዘገ**

ተምዘገዘገ ግ እየተወነጨፈ በሃይል ተወረወረ፣ ተስፈንጠረ፣ ተውዘገዘገ።

ተምዘግዛጊ ስ ተወንጫፊ፣ ባየር ላይ ሂያጅ።

አምዘገዘገ ግ በሃይል አስፈንጥሮ፣ አሽቀንጥሮ ወረወረ።

አመዘግዛጊ ያየር ላይ ጦር መሳሪያዎችን ከምድር ላይ መወንጨፊያ።

መዛለያ "ዘለለ¹" ስር ተመ.

መዛቂያ "ዛቀ" ስር ተመ.

መዛዝኝ (መዛዝይ) ስ ለማገርነት የሚያገለግል፣ መለል ያለ እሾሃም የእፅዋት አይነት።

መዝሙረኛ "ዘመረ" ስር ተመ.

መዝሙር ዝ.ከ.

መዝናኛ "ዘና" ስር ተመ.

መዝገበ ቃላት "መዘገበ" ስር ተመ.

መዝጊያ "ዘጋ" ስር ተመ.

መዞሪያ "ዞረ" ስር ተመ.

መዥረገ ግ ፍሬን ከዛፍ በብዛት ሸመጠጠ።

መዥረጠ ግ ሳበ፣ ጎትቶ አወጣ፣ ነቀለ፣ መዘዘ፣ አወለቀ።

መዥርጥ ስ ለኮሶ መድሃኒት ነው ተብሎ የሚወሰድ የእፅዋት አይነት።

መዥገር ስ 1 በእንስሳት ላይ በተለይ በጉያቸው አካባቢ የሚጣበቅና ደም የሚመጥ ተባይ። 2. (ዘይ.፣ ስድብ) ከያዘ የማይለቅ፣ መንቻካ ሰው።

መዥገር 1ኛ ፍቺ

መይሳ ቅ የሚመልስ፣ ወደኋላ የሚያስኬድ፣ እንዲያፈገፍግ የሚያደርግ። *መይሳው ካሳ።*

መደለያ "ደለለ¹" ስር ተመ.

መደላድል "ደለደለ" ስር ተመ.

መደመደ ግ 1. በመዶዶ ቆረጠ፣ አወደ። 2. አሳጥሮ ቆረጠ፣ ከመከመ። 3. አጠፋ፣ አወደመ፣ ደመሰሰ። 4. ምድማድ አበጀ።

መድመድ ስ ከአንድ ከነበረ ነገር የቀረ ምልክት፣ ስር፣ ቅሪት።

ምድማድ ስ መኖሪያ፣ ማረፊያ (ሰወር ያለ ቦታ)።

መደመር "ደመረ" ስር ተመ.

መደረቢያ "ደረበ" ስር ተመ.

መደርደሪያ "ደረደረ" ስር ተመ.

መደቅደቂያ "ደቀደቀ" ስር ተመ.

መደቆሻ "ደቆሰ" ስር ተመ.

መደበ ግ 1. መደብ ሰራ (ለመኝታና ለመቀመጫ፣ ለችግኝ ማፍሊያ)። 2. በተወሰነ መጠን ወይም ቁጥር፣ በተፈለገው አይነት ወይም በወገን በወገን ከፋፍሎ አስቀመጠ፣ ለየብቻ አደረገ፤ ደለደለ። 3. ለፈለገው ነገር ወይም ጉዳይ ለማዋል መጥና ወይም ወስና አዘጋጀ፣ አስቀመጠ። *ለወር ቀለብ መቶ ብር መድቧል።* 4. አሰማራ፣ ቦታ አስያዘ፣ ደለደለ። *የት መስሪያ ቤት መደቡህ?* 5. ገንዘብ ወይም ሌላ ነገር አስያዘ፣ ሰጠ፣ አስቀመጠ (ለቁማር)።

መደብ ስ 1. ልዩ ልዩ አትክልቶችን ለመዝራት ወይም ችግኞችን ለማፍላት ተቆፍሮ የለሰለሰና ከፍ ብሎ የተደለደለ መሬት ወይም አፈር። 2. (በተለይ በገጠር ቤቶች ውስጥ) በግድግዳ ጥግና በምሰሶ ዙሪያ ከመሬት ከፍ ብሎ ከጭቃ የሚሰራ መቀመጫ፣ መኝታ፣ ድልዳል። 3. በገበያ ቦታ አነስተኛ ነጋዴዎች ሸቀጣቸውን የሚደረድሩበትና የሚቀመጡበት ከፍ ተደርጎ የተደለደለ ስፍራ። 4. በተወሰነ ልክ ወይም መጠን ከተሸነሸነ፣ ከተከፈለ ነገር አንዱ ክፍል (ለምሳሌ የቅርጫ ስጋ መደብ)። 5. ከእቁብ፣ ከቁማር፣... ላይ ለአንድ ሰው የሚደርስ የአንድ ጊዜ ክፍያ። 6. ምራን የሚያርፍበት የቀንበር አማካይ ቦታ። 7. በንግግር ወይም በፅህፈት ጊዜ ስሙ፣ ተውላጠ ስሙ፣ ግሱ፣... የሚያመለክተው ሰው ደረጃ (አንደኛ መደብ እኔ፣ እኛ፣ ሁለተኛ መደብ አንተ፣ አንቺ፣ እናንተ ወዘተ. እንደሚለው ያለ)። 8. በላዩ ላይ ሌላ ነገር የሚሰራበት የመጀመሪያ ወይም ታችኛው መልክ። *መደቡ ጥቁር ሆኖ ቀይ አበባ ያለበት ጨርቅ።* 9. (ፖ.ኢኮ.) በአንድ በተወሰነ የእድገት ደረጃ ላይ በሚገኝ ህብረተሰብ ውስጥ በማምረት ተግባር ላይ ባለው ሚና፣ ከማምረቻ መሳሪያ ጋር ባለው ግንኙነት፣ ምርትን በመከፋፈል ረገድ ባለው ድርሻና ድርሻውን በሚያገኝበት ዘዴ አንዱ ከሌላው የሚለይበት የሰዎች ቡድን ወይም ክፍፍል። *የላብ አደሩ መደብ።*

መደበኛ ቅ ቋሚ፣ ዋነኛ። *ከመደበኛ ስራው ውጪ ይነግዳል።*

መደበኛ ስብሰባ ስ አንድ የፖለቲካ ወይም ሌላ ድርጅት ወይም ማህበር በተወሰነ ጊዜ በቋሚነት የሚያደርገው ስብሰባ። *በምክር ቤቱ 10ኛ መደበኛ ስብሰባ ብዙ ውሳኔዎች ተላልፈዋል።*

መደበኛ ቋንቋ ስ በአብዛኛው ህዝብ ዘንድ ተቀባይነት ያለውና የህብረተሰቡ አብዛኛው ክፍል የሚጠቀምበት ቋንቋ።

ምድብ ስ የስራ ቦታ፣ ክፍል።

ተመደበ ግ 1. በተወሰነ መጠን፣ በተፈላጊው አይነት ወይም በወገን በወገኑ ተከፋፍሎ ተቀመጠ፣ ለየብቻ ተደረገ። 2. ለተፈለገው ነገር ወይም ጉዳይ ለማዋል ተመጥኖ፣ ተወስኖ ተዘጋጀ፤ ተቀመጠ። 3. ስፍራ ያዘ፣ ተደለደለ።

መደብር ስ ሱቅ።

መደንቀሪያ "ደንቀረ" ስር ተመ.

መደንቆያ "ደነቆለ" ስር ተመ.

መደንጎሪያ "ደነጎረ" ስር ተመ.

መደወሪያ "ደወረ" ስር ተመ.

መደወተ ግ በሃይል መታ፣ ጠለዘ፣ ደወለ።

መደደቂያ "ደደቀ" ስር ተመ.

መደዳ ስ ተርታ፣ መት፣ ረድፍ።

መደዴ ስ (የን.አነ.) ያልተማረ፣ ያልሰለጠነ፣ ያልተገራ፣ ተራ ሰው።

መደገሻ "ደገሰ" ስር ተመ.

መደጎሻ "ደጎሰ" ስር ተመ.

መዲና^{1} ስ 1.ዋና ከተማ።2. ዋና መገኛ ማእከል፡ *አዲስ አበባ የቆንጆዎች መዲና ናት።*

መዲና^{2} ስ ብዙውን ጊዜ ይዘቱ ሃዘንና እንጉርጉሮ የሆነ ባለአራት ስንኝ የግጥም አይነት።

መዳ ስ ጣቃ፣ ጥቅል ጨርቅ።

መዳመጫ "ዳመጠ" ስር ተመ.

መዳረሻ "ደረሰ^{1}" ስር ተመ.

መዳሪያ "ዳረ" ስር ተመ.

መዳሻ "ዳሰ" ስር ተመ.

መዳብ ስ ቀይ ቡናማ መልክ ያለውና የኤሌክትሪክ ሃይልን በጥሩ ሁኔታ ሊያስተላልፉ ከሚችሉ ነገሮች አንዱ የሆነ የማእድን አይነት።

መዳኛ "ዳነ" ስር ተመ.

መዳፍ ስ ከወደ አውራ ጣት አካባቢ ያለው የውስጥ እጅ ታችኛው ክፍል።(ስእሉን እጅ ስር ተመ.)።

መድሃኒተኛ "ዳነ" ስር ተመ.

መድሃኒት ዝ.ክ.

መድህን ዝ.ክ.

መድሉ "አደላ" ስር ተመ.

መድረሻ "ደረሰ^{1}" ስር ተመ.

መድረክ ስ 1. በራፍ፣ ደፍ አጠገብ ያለ ቦታ። 2. በስብሰባ፣ በትያትር፣... አዳራሽ ውስጥ ተናጋሪው፣ ተዋናዩ፣... ለሁሉም እንዲታይ ለማድረግ ከወለሉ ከፍ ብሎ የተሰራ ቦታ። 3. በአንድ ጉዳይ ላይ ለመወያየት፣ ሃሳብ ለመስጠት፣... የተዘጋጀ ወይም የሚዘጋጅ አመቺ ሁኔታ።

መድበል ስ ጥንቅር፣ ስብስብ፣ ክምችት(ለምሳሌ

የቃላት መድበል)።

መድን (መድህን) "ዳነ" ስር ተመ.

መድፍ ስ አፈሙዙ ሰፊ የሆነ፣ ትልቅ ጥይት የሚጎርስና በርቀት ለመምታት የሚያስችል ከባድ መሳሪያ።

መድፈኛ ስ መድፍ የሚተኩስ ወይም የሚያስተኩስ የወታደር ክፍል።

መድፍን ፀር "ደፈነ" ስር ተመ.

መዶሻ ስ ብዙውን ጊዜ ከባድ የብረት ጭንቅላትና የብረት ወይም የእንጨት እጀታ ያለውና ምስማር ለመምታት፣ ድንጋይ ለመፈርከስ፣ የጎበጠ ብረትን ለማቃናት፣... የሚያገለግል የተለያየ መጠን ያለው መሳሪያ።



መዶሻ

መጀመሪያ "ጀመረ" ስር ተመ.

መጅ ስ 1. በመፍጮ ላይ ወደ ፊትና ወደ ኋላ በማመላለስ እህልን ለመከካት ወይም ለመፍጨት የሚያገለግል ትንሽ የወፍጮ ድንጋይ(ስእሉን ወፍጮ ስር ተመ.)። 2. በመፈጋፈግ የተነሳ የጠነከረ ወይም የደደረ የሰውነት ቆዳ። 3. በብጉንጅ ወይም በሌላ የቁስል አይነት ውስጥ የሚፈጠር የጠጠረ እብጠት።

መገለ ግ መግል ወጣ፣ ፈሰሰ።

መግል ስ ከቁስል ወይም በተለያየ ምክንያት ከተመረዘ የሰውነት ክፍል የሚወጣ ቢጫማ መልክ ያለው ወፈር ያለ ፈሳሽ።

አመገለ ግ መግል የያዘውን የሰውነት ክፍል በመጫን ወይም በማፍረጥ ፈሳሹ እንዲወጣ ወይም እንዲፈስ አደረገ።

መገለጢጥ "ገለጠጠ" ስር ተመ.

መገመገ ግ መጠመጠ፣ ለገለገ፣ ጠባ።

መገበ^{1} ግ ቀለበ፣ አበላ፣ አጠጣ።

መጋቢ ስ የአበምኔት ምክትል የሆነ የገዳም ሹም።

መጋቢ ወንዝ ስ ወደ ትልቅ ወንዝ የሚቀላቀል ትንሽ ወንዝ።

መጋቢት ስ በሴት ገዳም ውስጥ የመጋቢነት ማእረግ ያላት ሴት መነኩሲት።

ምግብ ስ 1. ሰዎች፣ እንስሳትና ተክሎች በህይወት ለመቆየትና ለማደግ የሚበሉት፣ የሚጠጡትና የሚወስዱት ማንኛውም ነገር። 2. እንደ መጠጥ፣ ውሃ፣ ያሉትን የሚጠጡ ነገሮችን የማይጨምር ማንኛውም የሚበላ ነገር።

ምግብ ቤት ስ 1. በማንኛውም ቤት ውስጥ ሊኖር የሚችልና ለምግብ መብያ ተብሎ የተዘጋጀ ክፍል። 2. ምግብ እየተዘጋጀ የሚሸጥበት ቤት፣ ሆቴል።

የምግብ ሸቀጥ ስ ለምግብነት የሚውል ሸቀጥ።

የምግብ ጠረጴዛ ስ ምግብ የሚበላበት ጠረጴዛ።

ተመገበ ግ በላ፣ ጠጣ።

መገበ^{2} ግ ገባ፣ ታየ (ኮከብ)። *ኣቅራብ የተባለው ኮከብ የጥቅምትን ወር ይመግባል።*

መገብተ ኣውራህ ስ የአስራ ሁለቱ ወራት ኮከቦች መጠሪያ። (እነዚሁም ሚዛን፣ ኣቅራብ፣ ቀውስ፣ ጀዲ፣ ደለዊ፣ ሁት፣ ሃመል፣ ሰውር፣ ገውዝ፣ ሸርጣን፣ አሰድና ሰንቡላ ናቸው)።



መገብተ ኣውራህ

መገበሪያ "ገበረ" ስር ተመ.

መገትሪያ "ገተረ" ስር ተመ.

መገናኛ "*ገነኘ" ስር ተመ.

መጋላ ቅ ጠይም (ለከብት)።

መጋልማ ቅ ጠይምነት ያለው (ለከብት)።

መጋረጃ "ጋረደ" ስር ተመ.

መጋቢ "መገበ^{1}" ስር ተመ.

መጋቢ ሃምሳ አለቃ ስ በወታደር ክፍል ውስጥ ከአስር አለቃ በላይና ከሃምሳ አለቃ በታች ያለ ማእረግ።

መጋቢት^{1} ስ ከየካቲት ወር ቀጥሎ የሚመጣ የአመቱ ሰባተኛ ወር ስም።

መጋቢት^{2} "መገበ^{1}" ስር ተመ.

መጋኛ ስ 1. የተዘጋን ቤት ከፍቶ በድንገት በመውጣት ወይም በመግባት፣ ከፍቱን ባደረ ውሃ በመታጠብ፣... የተነሳ ይመጣል ተብሎ

የሚታመንበት በሽታ። 2. (ዘይ.፥ ስድብ) ክፉ፥ ተንኮለኛ።

መጋዘን ስ የእቃ ማስቀመጫ ወይም ማከማቻ ክፍል።

መጋዝ ስ እንደ ማጭድ ጥርስ ያለውና እንጨት፥ ብረት፥... ለመቁረጥ የሚያገለግል፥ ሳሳ ካለ ብረት የተሰራና እጀታ ያለው መሳሪያ።



መጋዣ ስ 1.ለግልቢያ የማይሆን፥ ለጋርነት የሌለው የጭነት ፈረስ፥ አጋሰስ። 2. (ዘይ.፥ስድብ) መብላት የሚወድ፥ ሆዳም።

መጋፊያ "ጋፈ" ስር ተመ.

መግሰቦ ስ የአሳ ማጥመጃ።

መግለጫ "ገለጠ" ስር ተመ.

መግሳሊት ስ የማሰሮ ወይም የቶፋ ወይም የምንቸት ክዳን።

መግል "መገለ" ስር ተመ.

መግቢያ "ገባ" ስር ተመ.

መግነዝ "ገነዘ" ስር ተመ.

መግዣ "ገዛ" ስር ተመ.

መግፊያ "ገፋ" ስር ተመ.

መግነጢስ ስ ማግኔት።

መጎናጠፊያ "ጎነፀፈ" ስር "መጎናፀፊያ"ን ተመ.

መጎዝ ስ ቀፎ እየደፋ ማር የሚበላ፥ ከውሻ የሚያንስና ከድመት የሚበልጥ አራት እግር ያለው የዱር አውሬ።

መጎጥ ስ አይጠ መጎጥ።

መጎጥ አፍ ቅ (ስድብ) አፉ እንደ አይጠ መጎጥ ያሞጠሞጠ።

መጓጓዣ "*ጓዘ" ስር ተመ.

መጠለያ " ጠለለ" ስር ተመ.

መጠመጠ ግ 1. በጣም ጠባ፥ መገመገ፥ ለገለገ። 2. መጠጠ። 3. አጥብቆ ሳመ።

መጠቀ ግ 1. ከፍ አለ፥ ርቆ ወደላይ ወጣ፥ አረገ። 2. ረቀቀ፥ ጥልቀት አገኘ (በአስተሳሰብ፥ በእውቀት፥...)።

ምጥቀት ስ ጥልቀት፥ ብስለት።

አመጠቀ ግ ተኮሰ፥ ወደ ሕዋ ላከ (መንኮራኩርን)።

መጠቅለያ "ጠቀለለ" ስር ተመ.

መጠባበቂያ "ጠበቀ³" ስር ተመ.

መጠነ ግ 1. በቂ፥ ልክ ነው ብሎ ያሰበውን ያህል ሰፈረ፥ ገመተ። 2. ልክ ሆነ፥ በቃ። *ሱሪው ልብስ ላለመጠነው! ሰፍቶበታል።* 3. አቻ፥ ተስማሚ፥ እኩያ ሆነ። *ከማይመጣጠነው ሰው ጋር ጓደኝነት ጀምሯል።*

መጠን ስ 1.ልክ። 2.የአንድ ነገር ርዝመት ወይም አጥረት፥ ስፋት ወይም ጥበት፥ ውፍረት ወይም ቅጥነት፥ ብዛት ወይም ማነስ።

መጠን የሌለው በጣም ብዙ፥ ስፍር ቁጥር የሌለው።

በመጠኑ ተው.ግ. ሳይበዛ ወይም ሳያንስ በልኩ።

አለመጠን በብዛት፥ አለልክ። *ያለመጠን በልቶ ሆዱን ነመመው።*

ከመጠን በላይ ከሚያስፈልገው በላይ፥ በብዛት።

የመጠን ለውጥ ስ አንድ ነገር በአይነት ሳይሆን መጠኑን በመጨመር ወይም በመቀነስ የሚያሳየው ለውጥ።

መጠነኛ ቅ ያልበዛ ወይም ያላነሰ፥ ልከኛ።

ምጣኔ ሃብት ስ የአንድ አገር ጠቅላላ ሃብትና ቅስቃሴው፥ ኢኮኖሚ።

ምጥን ቅ 1. ያልበዛ ወይም ያላነሰ፥ ልከኛ። ስ 2.ምጥን [ሽሮ] ጨው፥ በርበሬ፥ ሽንኩርትና ቅመማቅመም ገብቶበት የተዘጋጀ የሽሮ ዱቄት።

ተመጠነ ግ ተለካ፥ ልኩ ተወሰኖ ተዘጋጀ።

የተመጠነ በልክ ተወስኖ የተዘጋጀ።

ተመጣጠነ ግ ተቀራረበ፥ ተስተካከለ፥ ተነፃፀረ (በመጠን፥ በጉልበት፥ በችሎታ፥...)።

የተመጣጠነ ሊይዝ የሚገባውን አስፈላጊ ነገሮች በሙሉ በተገቢው መጠን የያዘ (ምግብ፥ መጠጥ፥...)።

የተመጣጠነ ምግብ ስ ለሰውነት እድገትና ጤንነት አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ሁሉ የያዘ ምግብ።

ተመጣጣኝ ቅ የተቀራረበ፥ የተስተካከለ (በመጠን፥ በጉልበት፥ በችሎታ፥...)።

መጠይቅ "ጠየቀ" ስር ተመ.

መጠወተ "መፀወተ" ን ተመ.

መጠጊያ "*ጠጋ" ስር ተመ.

መጠጠ ግ 1. ጠባ፥ መጠመጠ፥ ሳበ። 2. ፈሳሽ

የሆነን ነገር ስቦ ወይም መጥጦ አደረቀ። 3. ጠፈፈ፣ ደረቀ። 4. ምጥምጥ አድርጎ ሳመ። 5. በጠቅላላ ጨረሰ፣ ፈጀ።

መጣጣ ቅ ወዝ የሌለው፣ ደረቅ።

ምጣጭ ስ ታኝኮ፣ ተመጦ የተተፋ፣ ብላቶ።

መጠጥ አለ ግ ጠፈፍ አለ፣ መድረቅ ጀመረ (ጭቃ፣ የታጠበ ልብስ፣...)።

መጠጥ ያለ 1. ጠፈጥ፣ ደረቅ ያለ። 2. በእድሜ በሰል ያለ።

ምጥጥ ያለ መጣጣ።

ምጥጥ አደረገ ግ1. በጣም አክሳ፣ ወዝ አሳጣ። 2. በሙሉ ጨረሰ።3.መጥምጦ ሳመ።

ተመጠጠ ግ ፈሳሹ ተስቦ ወጣ፣ ባዶ ቀረ፣ ደረቀ።

አመጠጠ ግ አደረቀ። *ጠረጴዛው ላይ የፈሰሰውን ውሃ በጨርቅ አምጥጫው።*

መጠጥ "ጠጣ" ስር ተመ.

መጠጪ ዝ.ከ.

መጡብሽ "መጣ" ስር ተመ.

መጢቃ ስ ዲቃላ (ለበግ፣ ለፍየል)።

መጣ ግ 1. ተናጋሪው ወይም "መጣ" ባዩ ወዳለበት አካባቢ ተራመደ፣ ተጓዘ፣ ቀረበ፣ ተጠጋ። 2. ቀድሞ ከሚገኝበት ወይም ከነበረበት ቦታ ተናጋሪው ባለበት አካባቢ ተገኘ። *ቤቱ ቀድሮ ከናዝሬት እዚህ መጥቷል።* 3. ከሄደበት ተመለሰ። 4. ተቃረበ፣ ተዳረሰ (ጊዜ)። *ክረምት መጣ።* 5. ትዝ አለ፣ ታወሰ፣ ፈለቀ (ሃሳብ)። *አንድ ሃሳብ መጣልኝ!* 6. ሆነ (የስሌት ውጤት)። *ሁለት ና ሁለት ሲደመር አራት ይመጣል።* 7. ያዘ፣ ሊወጣ ተቃረበ። *ሸንተ መጣ።* 8. ተፈጠረ፣ አጋጠመ፣ ደረሰ (ችግር፣ መከራ፣...)።

መጣበት ትነሳበት፣ ጀመረው (ንዴት፣ ቁጣ፣...)።

መጡብሽ ስ 1. ወደ ተረኛው ማህበረተኛ ቤት የሚገባ ወይም የገባ ፀበል ፀዲቅ። 2. ቶሎ የምትገል ስስ ምጣድ።

በሚመጣው በሚቀጥለው። *በሚመጣው ሳምንት እንገናኛለን።*

የመጣው ቢመጣ የሆነው ቢሆን፣ የፈለገው ችግር ቢደርስ።

መጣተኛ (መፃተኛ) ስ ለአገሩ እንግዳ ለሰው ባዳ የሆነ፣ ስደተኛ፣ ባይተዋር የሆነ (ሰው)።

መጤ ቅ 1. የአገር ተወላጅ ያልሆነ፣ ከሌላ ቦታ መጥቶ የሰፈረ። 2. አገር በቀል ያልሆነ።

አማጭ (አማጪ) ስ ለሴት ባል ወይም ለወንድ ሚስት የሚያመጣ፣ የሚያገናኝና የሚያጋባ ሰው አማላጅ፣ ሽማግሌ ።

አስመጭ ስ የተለያዩ ሸቀጦችን ከውጭ አገር ወደ አገር ውስጥ ለንግድ የሚያስገባ ግለሰብ ወይም ድርጅት።

አስመጭና ላኪ ስ የተለያዩ ሸቀጦችን በንግድ መልክ ከውጭ ወደ አገር ውስጥ የሚያስገባና ከአገር ውስጥ ደግሞ ወደ ውጭ አገር የሚልክ ግለሰብ ወይም ድርጅት።

መጣብር ስ ከነሃስ፣ ከብር፣ ከወርቅ ተሰርተው በፈረስ እቃ ላይ የሚሰፉ ጌጦች።

መጣብቅ "*ጠበቀ" ስር ተመ.

መጣያ "ጣለ" ስር ተመ.

መጣጣ^1 **(መፃፃ)** ስ ሆምጣጣ።

መጣጣ አይብ ስ በስብሳ፣ ሽንኩርትና ሌሎች ቅመማት ተጨምረውበት ለጥቂት ቀናት በደንብ በተከደነ እቃ ውስጥ ከቆየ በኋላ ለምግብነት የሚያገለግል አይብ።

መጣጣ^2 "**መጠጠ**" ስር ተመ.

መጣፍያ "ጣፈ" ስር ተመ.

መጣፍጥ ስ የወጥ ማጣፈጫ ቅመም፣ ነጭ አዝሙድ፣ ጥቁር አዝሙድ።

መጤ "መጣ" ስር ተመ.

መጥለቂያ "ጠለቀ^2" ስር ተመ.

መጥረቢያ "ጠረበ" ስር ተመ.

መጥረጊያ "ጠረገ" ስር ተመ.

መጥረያ "ጠራ^1" ስር ተመ.

መጥበሻ "ጠበሰ" ስር ተመ.

መጥኔ "ጠና" ስር ተመ.

መጥፎ "ጠፋ^1" ስር ተመ.

መጨለሰ (ሞጨለሰ) ግ ፀጉርን አስተኛ፣ ለሽ አደረገ (በቅባት፣ በውሃ፣...)።

መጭላላ (ምጭልስ) ቅ (በቅባት፣ በውሃ፣...) የተኛ፣ ለጥ ያለ ፀጉር።

ተመጨለሰ ግ ተኛ፣ ለጥ አለ (ፀጉር)።

መጨለፊያ "ጨለፈ" ስር ተመ.

መጨረሻ "ጨረሰ" ስር ተመ.

መጨቃ ስ ነጭና ጠንካራ ድንጋይ።

መጨቅጨቂት "ጨቀጨቀ^1" ስር ተመ.

መጨበጫ "ጨበጠ" ስር ተመ.

መጨኔ ስ 1. የፈረስ፣ የበቅሎ ቀላቢና ሰጋሚ። 2. (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ያጋፋሪ ምክትል።

መጨጊያ ስ መከዳ።

መጫሚያ "ጫማ^1" ስር ተመ.

መጫሪያ "ጫረ" ስር ተመ.

መጫኛ "ጫነ" ስር ተመ.

መጫወቻ “*ጫወተ” ስር ተመ.

መጭ ስ ግንዱም ሆነ ቅጠሉ ባጠቃላይ ኮግ የሚመስል የአረም አይነት።

መጭ በቅሉን "ሂጂ" ለማለት የሚነገር ቃል።

መጭ አለ ግ 1. በቅሉን "ሂጂ" አለ። 2. (ዘይ.) ፈጥኖ፣ ሮጦ ሄደ።

መጭላላ "መጨለለ" ስር ተመ.

መጭመቂያ "ጨመቀ" ስር ተመ.

መፀዳጃ "ፀዳ" ስር ተመ.

መፀዳጃ ቤት ዝ.ከ.

መፀወተ (መጠወተ) ግ ለድሃ፣ ለችግረኛ ቸረ፣ ሰጠ፣ ተዘከረ።

ምፅዋት (ምጥዋት) ስ ለተቸገረ፣ ለድሃ ወይም ለለማኝ የሚሰጥ ገንዘብ፣ ምግብ፣ ልብስ፣...።

ምፅዋተኛ (ምጥዋተኛ) ቅ ምፅዋት የሚሰጠው ድሃ፣ ችግረኛ፣ ለማኝ፣ ተመፅዋች።

ተመፀወተ (ተመጠወተ) ግ ምፅዋት ተቀበለ (ድሃ፣ ችግረኛ፣ ለማኝ)።

ተመፅዋች (ተመጥዋች) ቅ ምፅዋት ተቀባይ፣ ድሃ፣ ችግረኛ፣ ለማኝ፣ በምፅዋት የሚተዳደር (ሰው)።

***መፀደቀ**

ተመፃደቀ ግ ራሱን ከፍ ከፍ አደረገ፣ አኩራራ፣ ራሱን በራሱ አደነቀ፣ አመሰገነ (እንዲህ አድርጌ፣ እንዲህ ሰርቼ፣... በማለት)።

ተመፃዳቂ ቅ እንዲህ አድርጌ፣ እንዲህ ሰርቼ እያለ ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርግ፣ ራሱን የሚያደንቅ፣ የሚያመሰግን፣ ግብዝ።

አመፃደቀ ግ እንዲህ አድርጌ፣ እንዲህ ሰርቼ እያለ ራሱን ከፍ ከፍ አደረገ፣ አደነቀ፣ አመሰገነ።

መፀው ስ ከመስከረም 26 እስከ ታህሳስ 25 ቀን ያለው ወቅት፣ ጊዜ።

መፃተኛ "መጣ" ስር ተመ.

መፃጉእ ስ 1. የአልጋ ቁራኛ ሆኖ የሚኖር በሽተኛ፣ ሽባ። 2. ሰውነቱ እንደልቡ የማይታዘዝለት፣ በደረቱ ወይም በጀርባው አካባቢ እብጠት ያለበት አጭር፣ ጎበጥ ያለ ሰው።

መፃፃ "መጣጣ^{1}"ን ተመ.

መፅሃፍ "ፃፈ" ስር ተመ.

መፈናፈኛ "*ፈነፈነ" ስር ተመ.

መፈንቅለ መንግስት "ፈነቀለ" ስር ተመ.

መፎከር "ፎከረ" ስር ተመ.

መፋቂያ "ፋቀ^{1}" ስር ተመ.

መፍሉስ "ፈለሰ" ስር ተመ.

መፍትሄ "ፈታ" ስር ተመ.

ሙ የ"መ" ፊደል ካእብ ዘር።

ሙሃሂት (ሙሃይት) ስ በስተሳን ያለ የጭንና የዳሌ መገናኛ (ስእሉን ሰውነት ስር ተመ.)።

ሙሉ "ሞላ" ስር ተመ.

ሙላ ስ የጭንና የዳሌ መገናኛ፣ መታጠፊያ (ስእሉን ሰውነት ስር ተመ.)።

ሙልሙል "ሞለሞለ" ስር ተመ.

ሙልጭልጭ "*ሞለጨለጨ" ስር ተመ.

ሙሬ (ሙሪ) ስ 1. ፍሬው ጥቁር የሆነና ጤፍ የሚመስል የሳር አይነት። 2. ከሙሬ ወይም ከጓሳ፣... የተበጀ መጥረጊያ ወይም ኖራ መቀቢያ ቡሩሽ።



ሙሬ 2ኛ ፍቺ

ሙር ቅ የተማረና እውቀት ያለው ሆኖ ወፈፍ ስለሚያደርገው ብዙ የሚለፈልፍና የሚናገር፣ ንግግሩ ግን ፍሬ ነገር ያዘለ (ሰው)።

ሙርሙርት "ሞረሞረ^{2}" ስር ተመ.

ሙርዝኝ ቅ ችኩ፣ ነዝናዛ፣ ነገር ከያዘ የማይለቅ።

ሙርጥ ስ 1. ቂጥ። (ጎጃም)። 2. (ነውር) የወንድ ብልት።

ሙርጥ አወጣ ተሰነጠቀ (ምጣድ፣ ድስት)።

ሙሴ ስ 1. አምስቱን የኦሪት መፃህፍት የፃፈ የእስራኤል ነቢይ። 2. የሰንበቴ ወይም የፅዋ ማህበርተኞች ሊቀመንበር፣ አለቃ። 3. የመስፈሪያ አይነት (እስራ ስድስት ሙሴ አንድ ማድጋ ይሆናል)።

ሙስሊም "ሰለመ^{1}" ስር "እስላም"ን ተመ.

ሙስና^{1} ስ ውበት፣ ደምግባት፣ ላህይ።

ሙስና^{2} ስ ለኮሶ ትል መድሃኒት ይሆናል የሚባል በቆላ የሚበቅል የእፅዋት አይነት።

ሙስና^{3} ስ በስልጣን ወይም በስራ ድርሻ አላግባብ የመገልገል፣ የመጠቀም ወይም የመጥቀም ድርጊት።

ሙሻ ዘር^{1} ስ አንድ ላይ ተጣምረው የሚነገሩ ድርብ ስሞች። ለምሳሌ ጥርሰ ወርቅ/ቤተ መፃህፍት።

ሙሻ ዘር^{2} ስ ወጣትነት። ሙሻዘሩ ረገፈ።

ሙሻ ዘር^{3} ስ በጠመንጃ ወይም በሽጉጥ ቧንቧ ውስጥ የሚገኝ ክብ ሆኖ ክርክር ያለውና ጥይቷ ስትተኮስ እየተሽከረከረች እንድትሄድ የሚያደርግ

ነገር።

ሙሽ ስ በደጋማ አካባቢ የሚበቅል እንደ ቄጠማ ያለ ውስጠ ክፍት ሳር።

ሙሽሪት "ሞሸረ" ስር ተመ.

ሙሽራ ዝ.ክ.።

ሙሽሮ "ምሽሮ" ን ተመ.

ሙሽት "ሟሸ" ስር ተመ.

ሙሾ ስ ሰው በሞተ ጊዜ በአውራጅና በተቀባይ አማካይነት በግጥምና በዜማ እየታጀበ የሚካሄድ ለቅሶ።

ሙሾ አውራጅ ስ አልቃሽ፣ የለቅሶ ግጥምን በዜማ እያሰማ የሚያስለቅስ ሰው።

ሙቀት "ሞቀ" ስር ተመ.

ሙቀጫ "ወቀጠ" ስር ተመ.

ሙቅ "ሞቀ" ስር ተመ.

[የ] **ሙቅ መሬት** ስ ወላጅ ከልጆቹ መሃል አንዱን በመምረጥ የሚያወርሰውና ወራሹ ከሌሎቹ ልጆች ጋር የማይካፈለው ለመኖሪያው ቅርብና ጥሩ የሆነ አነስተኛ መሬት።

ሙታንታ (ሙታንቲ) ስ ከቀሚስ ወይም ከሱሪ ስር የሚለበስ፣ ገላ ላይ የሚያርፍ የውስጥ ሱሪ፤ ሃፍረተ ስጋን መሸፈኛ።

ሙት "ሞተ" ስር ተመ.

ሙትቻ ዝ.ክ.

ሙና ቅ ቆንጆ (ለትንሽ ልጅ)።

ሙናና "ሟነነ" ስር "ሞናና" ን ተመ.

ሙክራ "ሞከረ" ስር ተመ.

ሙክት "ሞከተ" ስር ተመ.

ሙክክ አለ "ሞክክ" ስር ተመ.

ሙዚቀኛ "ሞዘቀ" ስር ተመ.

ሙዚቃ ዝ.ክ.

ሙዚየም ስ የተለያዩ የታሪክ፣ የስነጥበብ፣ የሳይንስ፣... ቅርሶች ተሰብስበው የሚቀመጡበትና ለህዝብ እይታ የሚቀርቡበት ቤት።

ሙዜ "ሚዜ" ን ተመ.

ሙዝ ስ ሞለል ያለና ተልጦ የሚበላ ጣፋጭ የፍራፍሬ አይነት፤ ሙዙን የሚያፈራው ተክልም ሙዝ ይባላል።

ሙዝኝ "ሞዘዘ" ስር ተመ.

ሙያ (ሞያ) ስ 1. በአንድ በተወሰነ ስራ ላይ በልምድ ወይም በስልጠና የሚገኝ እውቀት፣ ችሎታ። 2. ቃላት በአረፍተ ነገር ውስጥ የሚሰሩት ስራና የሚሰጡት አገልግሎት (ለምሳሌ እንደ ቅፅል፣ ስም፣... በመሆን)።

ባለሙያ ስ 1. በአንድ በተወሰነ ስራ ላይ በልምድ፣ በስልጠና የተገኘ እውቀት፣ ችሎታ ያለው ሰው። 2. በቤት ባልትና ጥሩ ችሎታ ያለው ሰው (ብዙውን ጊዜ ለሴት)።

ሙያተኛ ቀ "ቀን ሙያተኛ"ን ተመ.

ሙያውን "ዋለ" ስር ተመ.

ሙዳ [ስጋ] ስ እየተመጠነ የተቆረጠ የስጋ ጉማጅ፣ ቁርጥ።

ሙዳይ ስ ሴቶች ብዙውን ጊዜ ለጌጣጌጥ፣ ለብርጉድ፣... ማስቀመጫ የሚገለገሉበት፣ በአገልግል ቅርፅ የምትሰራ አነስተኛ የስፌት እቃ።

ሙጃ ስ በክረምት ወራት በብዛት የሚበቅል የሳር አይነት።

ሙጃሌ (ሞያሌ) ስ ብዙውን ጊዜ እጅና እግር ቆዳ ውስጥ ሰርስራ የምትገባና የምታሳክክ ቁንጫ የምትመስል ተባይ።

ሙገሳ "*ሞገሰ" ስር ተመ.

ሙገጫ "ወቀጠ" ስር "ሙቀጫ"ን ተመ.

ሙጋድ (የሙጋድ እንጨት) ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) በቤተክርስቲያን ለመስዋእት መስሪያና ለማእጠንት ፍም የሚያገለግል የማገዶ እንጨት።

ሙግት "ሞገተ" ስር ተመ.

ሙግድ (ሞክድ፣ ሞግድ) ስ አክንባሎ።

ሙሳሳ "ምሳሳ" ን ተመ.

ሙጢ "*ሞጠሞጠ" ስር ተመ.

ሙጣጭ "ሟጠጠ"ስር ተመ.

ሙጥልቅ "ሞጠለቀ" ስር ተመ.

ሙጥኝ

[የ] **ሙጥኝ አለ** ግ 1. አድኑኝ፣ አስጥሉኝ ብሎ ተጠጋ። 2. አልለይ አለ፣ ተቆራኘ።

ሙጫ "ሞጨጨ" ስር ተመ.

ሙጫሌ ስ ትንሽ የሆነ ጨቅላ ልጅ (ሴቷ ሙጫሊት ትባላለች)።

ሙጭ ስ እንደ ገና ዱላ ከጫፉ ቆልመም ያለ የጤፍ መውቂያ እንጨት።

ሙጭራጭ ቅ አጭርና ቀጭን የሆነ፣ ከሳሳ።

ሙጭርጭር "ሟጨረ" ስር ተመ.

ሙጭጭ አለ "ሞጨጨ" ስር ተመ.

ሚ የ"መ" ፊደል ሳልስ ዘር።

ሚሊ

ሚሊ ሊትር ስ የፈሳሽ መጠን መለኪያ (1000 ሚሊ ሊትር 1 ሊትር ይሆናል)።

ሚሊ ሜትር ስ የርዝመት መለኪያ(1000 ሚሊ ሜትር 1 ሜትር ይሆናል)።

ሚሊግራም ስ የክብደት መለኪያ(1000 ሚሊ ግራም 1 ግራም ይሆናል)።

ሚሊዮነር ስ በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ያለው በጣም ሃብታም ሰው።

ሚሊዮን ስ አንድ ሺህ ጊዜ አንድ ሺህ (በቁጥር ሲፃፍ 1.000,000 ነው)።

ሚሳኤል ስ በፀደይ ወቅት የሚታይ የኮከብ ስም።

ሚሲዮን (ሚሽን) ስ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን በተለየ መልኩ የክርስትና ሃይማኖትን የሚከተሉና የሚያስፋፉ የውጭ ዜጎች የመሰረቱት የሃይማኖት ማስፋፊያ ድርጅት።

ሚሳይል ስ አንድን ነገር ለመደምሰስ የሚተኮስና ረጅም ርቀት ለመጓዝ የሚችል ተምዘግዛጊ የጦር መሳሪያ።

ሚስማር "ምስማር"ን ተመ.

ሚስት (ምሽት) ስ ከወንድ ጋር በህጋዊ ጋብቻ የተጣመረች ሴት፤ የወንድ የትዳር ጓደኛ።

ሚስጥር "*መስጠረ" ስር "ምስጢር"ን ተመ.

ሚኒ "ሚኒስከርት"ን ተመ.

ሚኒስቴር ስ በስሩ የተወሰኑ የስራ ዘርፎችን አካቶ የያዘና የመንግስትን አላማዎች፣ ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች የሚያስፈፅም የመንግስት መስሪያ ቤት። (ለምሳሌ የባህልና ማስታወቂያ ሚኒስቴር)።

ሚኒስትር ስ አንድን የሚኒስቴር መ/ስሪያ ቤት ለማስተዳደርና ለመምራት በመንግስት የሚሾም ከፍተኛ ባለስልጣን።

ሚኒስትሮች ምክር ቤት ስ የተለያዩ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች፥ ሚኒስትሮች አባል የሆኑበትና በጠቅላይ ሚኒስትር የሚመራ የመንግስት አካል፥ ጉባኤ።

ሚኒስከርት (ሚኒ) ስ ከጉልበት በላይ የሚውል በጣም አጭር ቀሚስ።

ሚና ስ 1.ቦታ፣ ጎራ። 2. የስራ ድርሻ።

ሚናውን ለየ ከሚመስለው፥ ከሚፈልገው ወገን በኩል ሆነ፤ አቋም ያዘ (በአስተሳሰብ፥ በድርጊት)።

ሚናውን ተጫወተ የሚጠበቅበትን የስራ ድርሻ አበረከተ።

ሚን ሚን አለ ግ ወዲያ ወዲህ አለ፤ ተወዛወዘ።

ሚክሮብ ስ በሽታን የሚያመጡና ለአይን የማይታዩ ጥቃቅን ህዋሳት።

ሚዛን "መዘነ"ስር ተመ.

ሚዛን ነፋስ ስ በመስከረም ወር የሚወጣ የኮከብ አይነት፤ በተጨማሪ "ኮከብ ቆጠራ"ን ተመ.

ሚዜ (ሙዜ) ስ ከሙሽሮች ጎን በቅርብ በመሆን የሰርጉን ስነ ስርአት የሚያካሂድ የሙሽሮች የቅርብ ጓደኛ።

ሚያው ድመት ስትጮህ የምታሰማው ድምፅ።

ሚያው አለች (ነውር) የወሲብ ስሜቷ በመነሳሳቱ ተቅበዘበዘች፥ ተባእት ፈለገች(ለሰው)።

ሚያው ብትል አታገኝም ምንም ብትሞክር፥ ብትለፋ አታገኝም።

ሚያዝያ ስ ከመጋቢት ቀጥሎ የሚመጣ የአመቱ ስምንተኛ ወር ስም።

ሚዳቋ ስ ፍየል የምትመስል አነስተኛ የዱር እንስሳ(ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።

ሚዶ ስ ከእንጨት፥ ከብረት ወይም ከፕላስቲክ የሚሰራ የፀጉር ማበጠሪያ።



ሚዶ

ሚጥሚጣ ስ 1. መጠኑ አነስተኛ የሆነና ሲበሉት በጣም የሚያቃጥል የበርበሬ ቃሪያ አይነት፤ ተክሉም ሚጥሚጣ ይባላል። 2. ከሚጥሚጣ (ከጨው፥ ከኮረሪማና ከሌሎች ቅመማ ቅመሞች ድብልቅ ጋር ተፈጭቶ) የሚዘጋጅ ማባያ። 3. (ዘይ.) ለፍላፊ ፥ ነገረኛ።

ማ^1 የ "መ" ፊደል ራብእ ዘር።

ማ^2 "ማን"ን ተመ.

ማ___ "መ___" ን ተመ.

—ማ^1 አንድ ነገር ያለበት ወይም የበዛበት መሆኑን ለማሳየት በቃል መጨረሻ የሚቀጠል ምእላድ። *ድንጋያማ፣ ፀሃያማ ።*

_ማ^2 የሚመስል ለማለት በቃል መጨረሻ ላይ የሚቀጠል ምእላድ። *ቡናማ፣ ነብርማ።*

ማህሌት ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) በከበሮና በፀናፅል እየታጀበ በዜማ የሚባል መንፈሳዊ መዝሙር፣ ምስጋና፥ ፀሎት።

ማህሌት ቆመ በማህሌት ስነ ስርአት ላይ ተገኝቶ ከመዘምራኑ ጋር አብሮ ዘመረ፣ አመሰገነ።

ማህበር ስ 1.ተመሳሳይ እምነት ያላቸው የተወሰኑ ሰዎች በፈጣሪ ወይም በሌላ ቅዱስ ስም በየተራ እየዘጋጁ በበአሉ ቀን አንድ ላይ በመገናኘት የሚቀምሱት የፀበል ፀዲቅ ዝግጅት፥ ግብዣ።2.የተወሰነ አላማን በአንድነት ለማራመድ ተመሳሳይ ፍላጎትና አቋም ያላቸው ሰዎች

ስብሰብና የተሰባሰቡበት ድርጅት (ለምሳሌ የሴቶች፣ የነጋዴዎች፣... ማህበር)።

ማህበር ይጠጣል የፅዋ ማህበር አለው።

ማህበር ገባ የማህበር አባል ሆነ።

ማህበረሰብ (ማህበራዊ ትስስር ያለው) በተወሰነ አካባቢ ወይም ቦታ የሚኖር ህዝብ።

የቆሎ ማህበር ስ የጠላ፣ የቆሎና የዳቦ ዝግጅት ብቻ የሚጠይቅ የፅዋ ማህበር።

የእንጀራ ማህበር ስ ድግሱ ዳቦና ጠላ ብቻ ሳይሆን እንጀራንም የሚጨምር የፅዋ ማህበር።

የፅዋ ማህበር የ"ማህበር"ን 1ኛ ፍቺ ተመ.

ማህበረተኛ ስ የማህበር አባል።

ማህበራዊ ቅ 1. የህብረት፣ የጋራ። 2. የህዝብ።

ማህደር ስ 1. አንድን ነገር ለማስቀመጫ ተብሎ ከቆዳ ወይም ከሌላ ነገር የተበጀ ሳጥን፣ ኪስ። 2. የመፅሃፉን ቅርፅ ይዞ ከቆዳ የሚዘጋጅ ባለማንጠልጠያ የመፅሃፍ መከተቻ፣ መያዣ (ለምሳሌ የዳዊት፣ የዜማ መፅሃፍ ማህደር)። 3. አንድን ሰው ወይም አንድን ጉዳይ ብቻ የሚመለከቱ ደብዳቤዎች፣ ሰነዶች፣... የሚቀመጡበት ፋይል፣ ዶሴ።

ማህፀን ስ በሴትና በአጥቢ እንስሳት ሆድ ውስጥ የሚገኝ፣ ፅንስ ለማደግና በህይወት ለመቆየት የሚያስፈልጉትን ነገሮች ከእናቱ እያገኘ የሚቆይበት የሰውነት ክፍል።



ማህፀን

ማህፀነ ክፉ የክፉ ወይም የመጥፎ ልጅ እናት።

ማህፀነ ደግ ጥሩ ጠባይ ያለው ወይም የደግ ልጅ እናት።

ማህፀኗ ተዘጋ/ተደፈነ 1. እንዳትወልድ ተደረገች። 2. መከነች።

ማህፀኗ ተፈታ መውለድ ቻለች።

ማለ ግ 1. የተናገረው እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ ወይም ለማሳመን እንዲህ ያድርገኝ፣ እንዲህ ይድረስብኝ ወይም እገሌ ይሙት፣... አለ። 2. አንድን ነገር ደግሜ አላደርግም በማለት በሚያመልከው ወይም በሚወደው ስም ተገዘተ፣ እርም አለ፣ ቃል ገባ።

ማላ (መሃላ) ስ አንድ ነገር እውነት መሆኑን ለማረጋገጥ፣ ለማሳመን እንዲህ ያድርገኝ፣ እንዲህ ይድረስብኝ፣ እገሌ ይሙት፣... በማለት ወይም አንድን ነገር ደግሜ አላደርግም በማለት በሚያመልኩት ወይም በሚወዱት ስም፣... የሚገባ ቃል።

ማላ አፈረሰ አላደርግም ወይም አደርጋለሁ ብሎ በመሃላ የሰጠውን ቃል ተወ፣ አፈረሰ።

ማላ ፉት በሆነ ባልሆነው በሃሰት የሚምል፣ መሃላ የማይፈራ።

ማለኛ ቅ ማላ የሚያበዛ።

ማለለ ግ ለመነ፣ ተማፀነ (ብዙውን ጊዜ በፀሎት)።

ተማለለ ዝ.ከ.

ማለቂያ "**አለቀ**" ስር ተመ.

ማለት "**አለ**" ስር ተመ.

ማለኛ "**ማለ**" ስር ተመ.

ማለዋወጫ "**ለወጠ**" ስር ተመ.

ማለደ^{1} ግ በጠዋት ተነሳ።

ማለዳ ስ በጣም ጠዋት።

ማላጅ ቅ በጠዋት መነሳት የሚወድ፣ የሚያዘወትር።

ማለደ^{2} ግ ለመነ፣ ደጅ ጠና።

መማለጃ ስ ጉቦ፣ እጅ መንሻ።

ምልጃ ስ ልመና፣ ደጅ ጥናት።

ተማለደ ግ ተለመነ፣ ይቅር አለ።

አማለደ ግ 1. አስታረቀ፣ ሸመገለ። 2. አንዱ ለሌላው ተለማኝ ለለማኙን ይቅርታ እንዲያደርግ ወይም የሚፈልገውን ጉዳይ እንዲፈፅምለት በለማኙ ስም ከተለማኙ ጠየቀ፣ ለመነ (ሶስተኛ ወገን በመሆን)።

አማላጅ ስ 1. አስታራቂ፣ ሽማግሌ። 2. አንዱ ለሌላው (ተለማኝ ለለማኝ) ይቅርታ እንዲያደርግ ወይም የሚፈልገውን እንዲፈፅምለት በለማኙ ስም ተለማኙን የሚጠይቅ፣ የሚለምን ሶስተኛ ወገን።

ማለዳ "**ማለደ**^{1}" ስር ተመ.

ማለገ ግ 1. ተገለገለ፣ ተሳበ (ፈሳሽነት ያለው ነገር)። 2. (ዘይ. ተስድብ) ማገጠ፣ ተሞላፈጠ።

ማላጋ ቅ 1. ዝልግልግ ያለ፣ የሚሳብ (ፈሳሽነት ያለው ነገር)። 2. (ዘይ.፣ ስድብ) ማጋጣ፣ ሞልፋጣ።

ማለፊያ "**አለፈ**" ስር ተመ.

ማላ "**ማለ**" ስር ተመ.

ማላሻ "**ላሰ**" ስር ተመ.

ማሳቀቂያ "**ለቀቀ**" ስር ተመ.

ማሳበሻ "ለበሰ" ስር ተመ.

ማሳጅ "ማለደ^{1}" ስር ተመ.

ማሳጋ "ማለገ" ስር ተመ.

ማልቀሻ "*ለቀሰ" ስር ተመ.

ማልድያ (ማልደያ) ስ ገዳዮች (አዳኞች) በእጃቸው ያደርጉት የነበረ ከመዳብ ወይም ከነሃስ፥... የሚሰራ የጎዳይ ምልክት፡ አምባር።

ማመሳለሻ "መለሰ" ስር ተመ.

ማመልከቻ "*መለከተ" ስር ተመ.

ማማ ስ ለጥበቃ ወይም አካባቢውን ለመቃኘት እንዲያመች ተብሎ በሰብል፡ በአዝመራ፡... መሃከል የሚተከል ረዥም ቆጥ።

ማማሰያ "መሰለ" ስር ተመ.

ማማት "ሀማማት" ን ተመ.

ማምለኪያ "መለከ"ስር ተመ.

ማምለጫ "*መለጠ" ስር ተመ.

ማምረቻ "መረተ^{1}" ስ ስር ተመ.

ማምሻ "መሸ" ስር ተመ.

ማሚጠጫ "ሚጠጠ" ስር ተመ.

ማሚጫ " ሚጨ" ስር ተመ.

ማረ ግ በማዘን ወይም በመራራት ይቅር አለ፡ ተወ፥ ምህረት አደረገ (በደልን፥ እዳን)።

መሃሪ (ማሪ) ቅ ይቅር ባይ፡ ምህረት የሚያደርግ።

ምህረት (ምረት) ስ ይቅርታ።

ማረሚያ "አረመ" ስር ተመ.

ማረሚያ ቤት ዝ.ከ.

ማረረ ግ ዞሮ ለመነ፥ ቃረመ።

ማራሪ ቅ ቃራሚ፡ ለማኝ።

ማረሳሻ "ረሳ" ስር ተመ.

ማረሻ "አረሰ^{1}" ስር ተመ.

ማሬሻ "አረሰ^{2}" ስር ተመ.

ማረበላ "ማር" ስር ተመ.

ማረከ ግ 1. በጦርነት ወይም በውጊያ ላይ ጠላቱን በቁጥጥር ስር አደረገ። 2. በምርኮ ወሰደ። 3. መሰጠ፡ ሳበ።

ምርኮ ስ በጦርነት ጊዜ በቁጥጥር ስር የዋለ የጠላት ወታደር፡ መሳሪያ፡ ንብረት።

ምርኮኛ ቅ 1. በጦርነት፥ በውጊያ ላይ በቁጥጥር ስር የዋለ የጠላት ወገን። 2. (ዘይ.) በአንድ ነገር ፍቅር የተያዘ፥ የተጠመደ።

ማረፌጅ "ማር" ስር "ማረበላ"ን ተመ.

ማረፊያ "አረፈ" ስር ተመ.

ማሪ "ማረ" ስር "መሃሪ"ን ተመ.

ማራምጣ "ማርአምጣ" ን ተመ.

ማራሪ "ማረረ" ስር ተመ.

ማራቶን ስ ከ42 ኪሎ ሜትር ጥቂት በለጥ የሚል ርቀት የሚሸፍን ከአለም አቀፍ ኦሎምፒክ የሩጫ ውድድሮች መካከል አንዱ።

ማራገቢያ "*ረገበ" ስር ተመ.

ማር ስ ንቦች አበባን በመቅሰም የሚያዘጋጁትና ወፍራም ፈሳሽ የሆነ ጣፋጭ ነገር። 2- (ዘይ.) ጣፋጭ፥ ደስ የሚል + የሚጥም።

ማር ቆረጠ ማርን ከቀፎው ውስጥ በሰለት እየቆረጠ አወጣ።

ማር ተሳሰ በበሰለ ወይም በከመጠጠ ጠላ ወይም በደረቀ ጠጅ ውስጥ ጠላውን ወይም ጠጁን ለማደስ ሲባል ማር ተጨመረበት።

ማር ነው ይጣፍጣል፡ ቆንጆ፡ ጥሩ ነው።

ማር ማር አለ ጣፈጠ።

ማርም አልስ በቃኝ፥ ጠግቢአለሁ፥ ከዚህ በላይ ምንም አልጨምርም።

ማረበላ (ማረፌጅ) ስ ማር የሚበላ ቀይ ጉንዳን።

ማርማሸላ ስ ባር ማሽላ፡ በቆሎ።

የማር ልጅ ስ የጡት ልጅ።

የማር እሸት ስ 1. አዲስ የተቆረጠ ትኩስ ማር። 2. በሰው መሬት ላይ ቀፎውን የሰቀለ ሰው ለባለ መሬቱ የሚሰጠው ማር።

የማር እንጀራ ስ ንቦች የሚጋግሩት (የሚያዘጋጁት) እንደእንጀራ አይን ያለው የማሩ ግግር።



የማር እንጀራ

ማርመላታ ስ እንደብርቱካን ወይም ሎሚ ወይም እንጆሪ፡... የመሳሰሉ ፍራፍሬዎችን ከስኳር ጋር ደባልቆ እስኪለደልድ በመቀቀል የሚዘጋጅ የዳቦ ማባያ።

ማርመጃ "አረመደ" ስር ተመ.

ማርስ ስ ከፀሃይ ጀምሮ ሲቆጠር በርቀት አራተኛ ሆና የምትገኝና በፀሃይ ዙሪያ ከሚሽከረከሩት አለማት ወይም ፕላኔቶች አንዷ።("ፕላኔት"ን ተመ.)።

ማርሻል ስ ከጀኔራል በላይ የሆነ ከፍተኛው

የወታደራዊ ማእረግ ስም::

ማርሽ^1 ስ የተሽከርካሪን ፍጥነት ለመለዋወጥ የሚያስችል ጥርሶች ያሉት የተሽከርካሪ ክፍል::

ማርሽ^2 ስ በአንድ ወታደራዊ ክፍል ውስጥ የሚገኝ የሙዚቃ ባንድ፣ የተለያዩ የሙዚቃ መሳሪያዎችን በመጠቀም በህብረት የሚጫወተው ሙዚቃ::

ማርትሬዛ ስ ማሪያ ቴሬዛ በተባለችው የነምሳ (ኦስትሪያ) ንግስት ስም በኦስትሪያ የተሰራ፣ በ19ኛው መቶ አመትና በ20ኛው መቶ አመት መጀመሪያ በኢትዮጵያ ይሰራበት የነበረ የመገበያያ ገንዘብ፤ ጠገራ ብር::

ማርአምጣ (ማራምጣ) ስ መንታ ጫፍ ያለው አለንጋ::

ማርከሻ "ረከሰ" ስር ተመ.

ማርክ ስ ለፈተና ውጤት የሚሰጥ ነጥብ::

ማርክሲዝም ስ በካርል ማርክስና በፍሬድሪክ ኢንግልስ የተቀመረ የሶሻሊዝም ፍልስፍና::

ማርክሲዝም ሌኒኒዝም ስ በካርል ማርክስና በፍሬድሪክ ኢንግልስ የተቀመረና በኋላ በሌኒን የዳበረ የሶሻሊዝም ፍልስፍና::

ማርያም (ድንግል ማርያም) ስ የኢየሱስ ክርስቶስ እናት::

ማርያም በሽልም ታውጣሽ (ምር.) ጠያቂዎች አራስ ሴትን ጠይቀው በሚወጡ ጊዜ ከአራስ ቤት በደህና አምረሽ ውጭ በማለት ለአራሷ የሚመኙላት የመልካም ምኞት መግለጫ::

ማርያም ጭንሽን ታሙቀው (ምር.) አራስ ሴት የአራስነት ጊዜዋን ጨርሳ በድጋሚ ለወሲባዊ ግንኙነት ብቁ እንድትሆን በመመኘት የሚነገር የመልካም ምኞት መግለጫ::

ማርያም የሳመችው በሰውነት ላይ በተፈጥሮ ጥቁር ሆኖ የሚገኝ እንደነጥብ ያለ አነስተኛ ምልክት::

በማርያም እጅ ተይዛለች እርጉዝ ነች::

የማርያም መቀነት ስ ቀስተዳመና::

የማርያም ምሳ ስ ሴት ስትወልድ የምትበላው የመጀመሪያው ገንፎ::

የማርያም ስፌት ስ ከብልት በታች ከፊንጢጣ በላይ የሚገኝ የተሰፋ የሚመስል የሰውነት ክፍል::

የማርያም ዘንግ ስ ቸርንችር፣ በትረሙሴ (በተለይ መነኩሲቶች እንደምርኩዝ ወይም እንደ መቋሚያ የሚጠቀሙበት የእፅዋት አይነት)::

የማርያም ግርዝ ስ በተፈጥሮው የተገረዘ ሆኖ የሚገኝ የሴት ብልት::

የማርያም ጠላት ስ 1.አባጨጓሬ:: 2. (ዘይ.) ሰው ሁሉ የሚጠላው ወይም ሰው ሁሉ ተሰብስቦ የሚደበድበው ሰው::

የማርያም ፈረስ ስ ከአንበጣ አነስ የሚልና ፌንጣ የሚመስል ነፍሳት::

የማርያም ፈረስ

ማርዬ ስ ከፈንጣጣ በሽታ አይነቶች የአንዱ ስም::

ማርዳ ስ ከብርና ከብርጭቆ መሰል ጌጥ የሚሰራ የልጆች የአንገት ጌጥ::

ማርገብገቢያ "*ረገበ" ስር ተመ.

ማርገጃ "ረገደ" ስር ተመ.

ማርጋሪን ስ ቅባትነት ካለው ስጋ ወይም ከአትክልት የሚሰራ ቅቤ::

ማርጣ ስ የዝሆን ጭራ::

ማሰ ግ ቆፈረ፣ ጉድጓድ አበጀ::

ማሳ ስ የታረሰ መሬት፣ እርሻ::

ማሰሮ ስ ለውሃ ማሞቂያ፣ ለንፍሮ መቀቀያ፣... የሚያገለግል የሸክላ እቃ፤ ምንቸት፣ ቶፋ (ስእሉን የሸክላ እቃ ስር ተመ.)::

ማሰሻ ስ **"አሰሰ"** ስር ተመ.

ማሰነ ግ ሰፋ፣ ደከመ::

ማሲንቆ(መሰንቆ) ስ ከእንጨት፣ ከፍየል ቆዳና ከፈረስ ጭራ የሚሰራ ባለአንድ ክር ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ (ስእሉን የሙዚቃ መሳሪያ ስር ተመ.)::

ማሳ "ማሰ" ስር ተመ.

ማሳሰቢያ "አሰበ" ስር ተመ.

ማስለቀሻ "*ለቀሰ" ስር ተመ.

ማስለቀቂያ "ለቀቀ" ስር ተመ.

ማስመሪያ "*ሰመረ" ስር ተመ.

ማስረጃ "*ረዳ" ስር ተመ.

ማስተንፈሻ "ተነፈሰ" ስር ተመ.

ማስተዛዘኛ "አዘነ" ስር ተመ.

ማስቲካ "መስቲካ" ን ተመ.

ማስታወሻ "*ታወሰ" ስር ተመ.

ማስታወቂያ "አወቀ" ስር ተመ.

ማስታገሻ "ታገሰ" ስር ተመ.

ማስገንዘቢያ "*ገነዘበ" ስር ተመ.

ማስጠንቀቂያ "ጠነቀቀ" ስር ተመ.

ማስጫ "*ሰጣ" ስር ተመ.

ማስፈራሪያ ፊት "ፈራ" ስር ተመ.

ማሻሻያ "*ሻለ" ስር ተመ.

ማሽላ ስ የፍሬው ቅርፅ ዘንጋዳ የሚመስልና የሚያክል ለእንጀራ፣ ለንፍሮ፣ ለጠላ የሚሆን በቆላና በወይና ደጋ የሚበቅል የአገዳ እህል።

ማሽን ስ 1. አንድን ተግባር በቀላሉና በፍጥነት ለማከናወን የሚያስችል፣ በነዳጅ፣ በኤሌክትሪክ፣... ሃይል የሚንቀሳቀስ ዘመናዊ መሳሪያ (ለምሳሌ የሹራብ መስሪያ፣ የጫማ መስፊያ ማሽን)። 2. ለዚህ ስራ ተብሎ በተዘጋጀ መሳሪያ ሽብሽቡ ከካውያ ስፌት ይበልጥ ጥቅጥቅ ብሎ የተሰራ ጉርድ ወይም ሙሉ ቀሚስ።

ማሽንክ ስ ሽረኛ፣ ተንኮለኛ፣ መሰሪ።

ማሾ ስ እንደፋኖስ ያለ ሆኖ ብርሃኑ ግን ከፋኖስ የሚበልጥ፣ በነጭ ጋዝ የሚበራ መብራት።

ማሾ

ማቀቀ ግ በበሽታ፣ በችግር፣... ተሰቃየ፣ መከራ አየ።

ማቀባበያ "*ቀበለ"ስር ተመ.

ማቀናነሻ "ቀነሰ" ስር ተመ.

ማቀዝቀዣ "ቀዘቀዘ" ስር ተመ.

ማቀፊያ "አቀፈ" ስር ተመ.

ማቆላሊያ "ቆላ^1" ስር ተመ.

ማቆረጫ "ቆረጠ" ስር ተመ.

ማቅ ስ ከጥቁር በግ ፀጉር ተፈትሎ የሚሰራ እንደ ብርድ ልብስ ያለ ልብስ።

ማቅ ለበሰ ራሱን በመጉዳት፣ በማጎሳቆል በጣም አዘነ።

ማቅረቢያ "ቀረበ" ስር ተመ.

ማቋቻ "ቋተ" ስር ተመ.

ማበረታቻ "በረታ" ስር ተመ.

ማበቻ "አበተ^1" ስር ተመ.

ማበጠሪያ^1 "*በጠረ^1" ስር ተመ.

ማበጠሪያ^2 "**በጠረ^2" ስር ተመ.

ማቡኪያ "ቦካ" ስር ተመ.

ማባበያ "**ባበለ" ስር ተመ.

ማባዛት"በዛ" ስር "**ማብዛት**"ን ተመ.

ማብረጃ "በረደ" ስር ተመ.

ማብሪያና ማጥፊያ "በራ" ስር ተመ.

ማብራሪያ ዝ.ክ.

ማብሰያ "በሰለ" ስር ተመ.

ማብዛት "በዛ" ስር ተመ.

ማተሚያ "አተመ" ስር ተመ.

ማተረ ግ 1. ቃኘ፣ ዙሪያውን አየ። 2. አሻግሮ አየ፣ ተመለከተ።

አማተረ ግ አሻግሮ አየ፣ ተመለከተ።

ማተብ ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) አንድ ሰው ክርስትና ሲነሳ ለሃይማኖት ምልክትነት በአንገቱ ላይ የሚያስረው ክር።

ለማተቡ ሲል ለሃይማኖቱ፣ ለእምነቱ ሲል።

ማተቡን በጠሰ 1. ካደ፣ እምነት አጎደለ። 2. ሰለመ።

ማተበ ቢስ እምነተ ቢስ፣ ከሃዲ።

ማተብ የለሽ ዝ.ክ.

ማቲ ስ ብዛት ያላቸው ትንንሽ ልጆች፣ ውሪ።

ማታ ስ ጀንበር ከጠለቀችበት አንስቶ እስከ ምሽቱ አምስት ሰአት ገደማ ያለው የጨለማ ጊዜ።

የማታ ማታ የኋላ ኋላ፣ በስተመጨረሻ።

የማታ ትምህርት ስ በትምህርት ቤት ውስጥ ማታ ማታ የሚሰጥ ትምህርት።

የማታ እንጀራ እድሜ ከገፋ በኋላ የሚገኝ ሃብት፣ ንብረት።

ማታለያ "*ታለለ" ስር ተመ.

ማትሪክ ስ የአስራ ሁለተኛ ክፍል መልቀቂያ ብሄራዊ ፈተና።

ማቶት ስ ክብ ሆኖ የተሰራ የእንስራ ወይም የጀበና፣...መቀመጫ።

ማነቆ "አነቀ" ስር ተመ.

ማን (ማ) ተው.ስ. 1. የትኛው ሰው ብሎ ለመጠየቅ የሚያገለግል ቃል። *ማን መጥቶ ነበር?* 2. መጠሪያ ስምን መጠየቂያ ቃል። *ስምህ ማን ነው? ዛሬ ማን ነው?*

ማን ላከብኝ ማን ሰደደብኝ፣ አዘዘብኝ (መጥፎ ነገር ወይም ጉዳት እንዲያደርስብኝ)።

ማንአለብኝነት ከኔ በላይ ማንም የለም፣ ማን ያዘኛል፣ ማን ይደፍረኛል ባይነት፣ ትእቢተኝነት።

ማን አባቱ(ማናባቱ) የትኛው፣ እንዴት ያለው ገዢ ለማለት የሚሰነዘር የንቀት፣ የማስፈራሪያ፣ የድንፋታ አባባል።

ማንዘራሽ 1. (ስድብ) የመጣበትና የወለደው ሰው የማይታወቅ፣ ምናምንቴ ብሎ ሰውን ለማኮሰስ የሚሰነዘር የንቀት አነጋገር። 2. መደዴ፣ ዱርዬ፣ ስነስርአት የጎደለው።

ማናቸውም(ማንኛቸውም) አንዳቸውም።

ማናቸውም መሄድ አይፈልጉም።

ማንም 1. የትኛውም፥ ማንኛውም፤ ሁሉም። 2.የማይታወቅ ሰው። *ማንም በወሰደው እኔ አልጠየቅም።* 3. ተራ ሰው፤ መደዴ። *ማንም ተነስቶ ላዋቂ ነኝ ይላል።*

ማንም የለም አንድም ሰው የለም።

ማንትስ (ማንትሴ) ተው.ስ. በአደናጋሪና አልታወስ ባለ ስም ምትክ በመግባት የሚያገለግል ቃል።

ማንነት ግለሰባዊ ምንነት (በባህርይ፤ በጠባይ፤ በችሎታ፤...)።

ማንነቱ ያልታወቀ ማን መሆኑ ያልታወቀ።

ማንነቴን አሳይሃለሁ ሃይሌን ወይም ችሎታዬን፥... አሳይሃለሁ፤ እንድታውቅ አደርግሃለሁ።

ማንኛቸው (ማናቸው) ከሁለቱ ወይም ከብዙዎቹ ውስጥ የትኛው።

ማንኛቸውም ማናቸውም።

ማንኛው የትኛው፤ የቱ።

ለማንኛውም 1. ማንንም ሳይለይ፤ ለሁሉም። *ለማንኛውም ሰው ይሸጣል።* 2. ቢሆንም ባይሆንም፤ ለሁሉም። *ለማንኛውም ሄደን ማየቱ ይሻላል።*

በማንኛውም መንገድ በየትኛውም አይነት፤ ሁኔታ።

ማንቀርቀቢያ "*ቀረቀበ" ስር ተመ.

ማንቁርት ስ በሰዎች ጉሮሮ (በተለይ በወንዶች) ላይ በውጭ በኩል እንደ ጉጥ ወጣ ብሎ የሚታየው የሰውነት ክፍል (ስእሉን ራስ ስር ተመ.)።

ማንቁርቱን ያዘው በሃይል አስጨንቆ ያዘው፤ አስገደደው (አንድን ነገር እንዲፈፅም)።

ማንቁርታም ቅ ማንቁርቱ ትልቅ የሆነ ሰው።

ማንቆርቆሪያ "*ቆረቆረ" ስር ተመ.

ማንኪያ ስ ከብረት ወይም ከእንጨት ወይም ከነሃስ ወይም ከፕላስቲክ፥... በአንድ በኩል እጀታ ኖሮት በሌላ በኩል ቀነፍና ጎድጓድ እንዲል ተደርጎ የተሰራ ለመቆንጠሪያ፥ ለመመገቢያ፥ ለመለወሻ፥... የሚያገለግል እቃ።



ማንኪያ

ማንደጃ "ነደደ" ስር ተመ.

ማንገቻ "አነገተ" ስር ተመ.

ማንጎ ስ በውስጡ ጠፍጠፍ ያለ ጠንካራ ፍሬ ያለው፥ እንደኮክ ተልጦና ተግጦ የሚበላ ጣፋጭ ፍሬ፤ ማንጎውን የሚያፈራው ተክልም ማንጎ ይባላል(ስእሉን ፍራፍሬ ስር ተመ.)።

ማንጓጠጥ "*ጓጠጠ" ስር ተመ.

ማኛ [ጤፍ] ስ በጣም ነጭ የሆነ ጤፍ።

ማእረግ ስ 1. ሹመት፥ ስልጣን፤ ደረጃ። 2. ክብር።

ማእረገቢስ ውርደት እንጂ ክብር የማይወድ፤ ክብረቢስ።

ማእረግ እሌቱ ዝ.ከ.

ማእበል ስ ሃይለኛ ነፋስ በባህር፥ በውቅያኖስ፥... ላይ የሚፈጥረው የውሃ መናወጥ፤ ሞገድ።

ማእከላዊ "*ማከለ" ስር ተመ.

ማእከል ዝ.ከ.

ማእዘን ስ 1. የማድማዳ መጨረሻ ወይም መታጠፊያ ጥግ ወይም የግድግዳዎች መገናኛ። 2. ሁለት መስመሮች የሚገናኙበት ቦታ። 3. አራት ገፅ ያለው ወፍራም ጥርብ እንጨት። 4. አቅጣጫ (ምስራቅ፥ ምእራብ፤ ሰሜን፤ ደቡብ)።



ማእዘን

የማእዘን ምት ስ (ስፖ.) በእግር ኳስ ጨዋታ ላይ፥ ኳስ በራስ ግብ አካባቢ ከግራው የማእዘን መታጠፊያ እስከ ቀኙ የማእዘን መታጠፊያ ባለው መስመር፤ በራስ ተጫዋቾች ወደ ውጪ ሲወጣ ለተቃራኒው ቡድን የሚሰጥ የቅጣት ምት።

ምእዙን ቅ አራት ማእዘንነት ያለው።

ማእድ(ማድ) ስ ለመብል የቀረበ ምግብ እስከ ማቅረቢያው፤ ገበታ።

ማእድ ረገጠ አብሮ ሲበላ ቆይቶ ማእዱ ሳይነሳ አቋርጦ ተነሳ፤ ሄደ።

ማእድ ወርዷል ምግብ ቀርቧል።

ማእድ(ማድ) ቤት ስ ምግብ የሚዘጋጅበት፥

የሚበስልበት ቤት፡ ኩሽና።

ማደኛ ስ ብዙ ጊዜ አብሮ የሚበላ የቅርብ ጓደኛ።

ማእድን ስ እንደወርቅ፣ ብር፣ ነሃስ፣ ብረት፣... ያለ ከመሬት ውስጥ የሚገኝ ንጥረ ነገር።

ማእዶት ስ በፋሲካ ማግስት የሚውለው ሰኞ።

ማእጠንት "አጠነ" ስር ተመ.

***ማከለ**

መካከል (መሃከል፣ መሃል) ቅ 1.አንድ ክብነት ያለው ነገር ከተለያዩ ጫፎች ወደ ውስጥ ሲለካ ሁሉም ጫፎች እኩል ርቀት ላይ የሚገናኙበት ቦታ። 2. የአንድ ነገር አጋማሽ፣ አማካይ ቦታ። 3. ዳር ያልሆነ፤ በሌሎች ግልቃ ያለ።

በመሃሉ (በመካከሉ) 1. አንድ ነገር በመከናወን ወይም በመካሄድ ላይ እያለ። *ስብሰባው እየተካሄደ በመሃሉ ተነስቶ ሄደ።* 2. በግልቃ። *በመሃሉ (በመካከሉ) ነው ያለበት ቢጫ ወርቅ።* 3. ከሁለት የተለያዩ ወይም ተቃራኒ ወገኖች በአንዱ ሳይሆን፤ በተገኘው አጋጣሚ። *እነሱ ሲጣሉ በመሃሉ እሱ ተጠቀመ።*

በመሃል ቤት ከሁለት የተለያዩ ወይም ተቃራኒ ወገኖች ወይም ጉዳዮች በአንዱ ሳይሆን፤ በመሃል።

መሃል ራስ ስ አናት፣ እርግብግቢት።

መሃል ሰፋሪ ቅ ከተቃራኒ ወገኖች ያንደኛውንም አቋም የማይከተል ወይም የማይደግፍ፣ ገለልተኛ፤ ከሁለቱም ያልወገነ።

መሃል አገዳ ስ 1. መሃል አጥንት (የቅልጥም፣ የጭን፣ የክንድ)። 2. በፊት እግር ቅልጥም መሃል ላይ የሚገኝ የከብት ስጋ።

መሃል እጅ ስ በመዳፍና በጣት መካከል ያለው ውስጠኛው የእጅ ክፍል።

መሃል ዳኛ ስ ችሎት ላይ ሆነው ፍርድ በሚሰጡበት ጊዜ በግራና በቀኝ ዳኞች መካከል የሚቀመጥና በስልጣን ከሁለቱ ዳኞች የሚበልጥ ዳኛ።

መካከለኛ (መሃከለኛ) ቅ 1.በመካከል የሚገኝ ወይም ያለ። 2. አይነቱ ወይም መጠኑ ወይም ሁኔታው፣... ከፍተኛ ያልሆነ ወይም ያልበዛ ወይም ያላነሰ፤ መጠነኛ።

ማእከል ስ 1. የተለያዩ እንቅስቃሴዎችና ተግባራት በከፍተኛ ደረጃ የሚከናወኑበት ቦታ። *የንግድ ማእከል።* 2. ተቋም። *የባህል ማእከል፤ የጤና ማእከል።*

ማእከላዊ ቅ 1. ለተለያዩ ወገኖች የጋራ የሆነ። 2. ለተለያዩ ወገኖች የበላይ የሆነ።

ማእከላዊ መንግስት ስ የተለያዩ አስተዳደሮችን፣ የፌዴራል ግዛቶችን፣... በበላይነት የሚያስተዳድር ወይም የሚመራ የአንድ አገር መንግስት።

ማእከላዊ አሰራር ስ ለተለያዩ ወገኖች የጋራ የሆነና አንድ አይነት መስመር የተከተለ አሰራር።

ተማከለ ግ የተለያዩ ድርጅቶች፣ አካላቶች፣... አሰራር በአንድ አይነት የበላይ አመራር ስር እንዲውል ተደረገ።

አማከለ ግ በሁለት የተለያዩ ወይም ተቃራኒ ነገሮች መሃል እንደ አገናኝ፣ አዛማጅ፣... ሆኖ ተገኘ፣ በመሃል ሆነ።

አማካይ ቅ 1. ለሁሉም የጋራ የሆነ፤ በመሃል ያለ። 2. አጋማሽ።

በ___ አማካይነት 1. በ___ ምክንያት። *በቫይረስ አማካይነት የሚመጣ በሽታ።* 2.በ___ በኩል። *በወንድሙ አማካይነት ጉዳዩ ተፈጸመለት።*

ማከፋፈያ "ከፈለ" ስር ተመ.

ማኩታ ስ 1. ስእለት፣ መሳለጃ። 2. መቆያ፣ መክሰስ።

ማኪያቶ ስ መጠኑ በርከት ባለ የፈላ ቡና ውስጥ ትንሽ ወተት ተደባልቆበት የሚዘጋጅ የመጠጥ አይነት።

ማካፈል "ከፈለ" ስር ተመ.

ማክሰኞ ስ በሰኞና በረቡእ መካከል ያለው ቀን ስም፤ ከእሁድ ጀምሮ ሲቆጠር የሳምንቱ ሶስተኛ ቀን።

ማኩብኮቢያ "*ኮበኮበ" ስር ተመ.

ማወራረጃ "ወረደ" ስር ተመ.

ማዋለጃ ክፍል "ወለደ" ስር ተመ.

ማውጫ "ወጣ" ስር ተመ.

ማዘንት ስ ክብ ሆኖ ከጭቃ የሚሰራ አመድ አቃፊ የምድጃ ዙሪያ።

ማዘያ "አዘለ" ስር ተመ.

ማዘዣ "አዘዘ" ስር ተመ.

ማዘጋጃ ቤት "*ዘገጀ" ስር ተመ.

ማዝ "አይን" ስር **"አይነ ማዝን"** ተመ.

ማዞሪያ "ዞረ" ስር ተመ.

ማዥራት "ማጅራት" ን ተመ.

ማይል ስ የርቀት መለኪያ። *አንድ ማይል 1.6 ኪሎሜትር ያህል ነው።*

ማይም "መሃይም" ን ተመ.

ማይካ ስ እንደሳህን፣ ኩባያ፣ ባልዲ ያሉትን ቁሳቁሶች ለመስራት የሚያገለግል፣ መለመጥና ብርሃን ማሳለፍ የሚችል ጥሬ እቃ።

ማይክሮስኮፕ ስ በጣም ጥቃቅንና ረቂቅ የሆኑ

ነገሮችን አጉልቶ የሚያሳይ መነፅር።

ማደሪያ "አደረ" ስር ተመ.

ማደሪያ መሬት ስ በቀድሞ የመሬት ስሪት ስርአት ውስጥ መተዳደሪያ እንዲሆን ለንጉስ አገልጋዮች ከንጉስ ይሰጥ የነበረ፥ እፅመ ርስት ያልሆነ መሬት።

ማደንዘዣ "ደነዘዘ" ስር ተመ.

ማደኛ "ማእድ" ስር ተመ.

ማደያ "አደለ" ስር ተመ.

ማደጎ "አደገ" ስር ተመ.

ማዳበሪያ "ዳበረ" ስር ተመ.

ማዳወሪያ "ደወረ" ስር ተመ.

ማድ "ማእድ" ስር ተመ.

ማድቤት ዝ.ክ.

ማድያት ስ የፊት ቆዳን የተፈጥሮ ቀለም የሚለውጥና የሚያጠቁር በሽታ።

ማድጋ ስ 1. ከእንስራ ከፍ ከጋን አነስ የሚል የሸክላ እቃ። 2. እስር ቀና ያህል የሚይዝ የእህል መስፈሪያ፥ መለኪያ።

ማጆ ስ 1. በወዲያ በኩል (ከወንዝ፥ ከተራራ፥...) አልፎ ወይም ተሻግሮ ያለ ቦታ። 2. ራቅ ብሎ ያለ ቦታ።

ማጀት ስ ብዙ ጊዜ በአነስተኛ ጎጆ ቤቶች ውስጥ በመከታ የተከለለ የእቃ መቀመጫ፥ ጓዳ።

ማጀራት (ማዥራት) ስ የአንገት ሄሳ ክፍል፤ ደንደስ። (ስእሉን ራስ ስር ተመ.)።

ማጀራት መቺ ቅ ብዙውን ጊዜ በጨለማ ቦታ አድፍጦና ደብድቦ የሚዘርፍ ቀማኛ።

ማገ ግ 1. ሰቦ፥ ምጥጥ አድርጎ ጠጣ። 2. ወደ ውስጥ ሳበ፥ አስገባ (ለምሳሌ አየርን)። 3. ፈሳሽ ነገርን መጠጠ፥ ያዘ፥ ራሰ።

አማገ ግ 1. ምግብ በሚበላበት ጊዜ የሚጠጣ ነገርን (ውሃ፥ ወተት፥...) ቶት እያለ ተመገበ።

ማገረ ግ ለግድግዳ፥ ለአጥር ተብሎ በቆመ እንጨት ላይ ማገርን በገመድ፥ በልጥ፥... በማሰር ወይም በምስማር በመምታት አያያዘ።

ማገር ስ በግድግዳ፥ በአጥር፥... ላይ አግድም የታሰረ ወይም በምስማር ወይም በሌላ ነገር የተያያዘ እንጨት፥ ብረት፥...።

ተማገረ ግ በማገር ታሰረ (ግድግዳ፥ጣራ፥...)።

ማገደ ግ 1. እሳት ውስጥ ከተተ፥ አነደደ። 2. ለአደጋ ወይም ለችግር ዳረገ።

ማገዶ ስ ለማብሰል፥ ለመቀቀል፥... የሚነድ እንጨት፥ ኩበት፥ ከሰል፥...።

ማገገሚያ "*ገገመ" ስር ተመ.

ማገጠ ግ 1. ባለገ፥ ተባለሸ፥ ዋልጌ ሆነ።2. አመነዘረ። 3. ጥሩ ሆኖ ሳይታረስ ቀረ (መሬት)።

አማገጠ ግ 1. ስራፈት አደረገ፥ አስነፈ፥ አባለገ፥ አበላሸ። 2. ወሲብ ፈፀመ፥ ወሸመ፥ አባለገ።

ማገጥ ስ መጠኑም ሆነ ቅጠሉ እንደ አብሽ ያለ፥ አብዛኛውን ጊዜ ከሳር ጋር አብሮ የሚበቅል፥ ፍሬው በደንብ ከመብሰሉ በፊት ከብቶች ከበሉት ሆዳቸውን የሚነፋና ለሞት የሚያደርስ የእፅዋት አይነት።

ማጉሊያ "ጎላ^{3}" ስር ተመ.

ማግ ስ 1. በእጅ እየተፈተለ በእንዝርት ላይ የሚጠመጠም፥ ከድር የሚወፍርና ሳሳ ያለ የጥጥ ክር። 2. በጣም ወይም በጥቅል መልክ እየተመረተ በሚወጣ ጨርቅ ላይ በወርዱ በኩል ከድሩ ጋር ተሰባጥሮ የሚገኘው ፈትል ወይም ክር።

ማግስት ስ ቀጥሎ የሚመጣው ቀን፥ በበነጋው። *ልጁ በመጣ በማግስቱ አባትየው ሄደ።*

ማግኔት ስ ብረትን የሚስብ ብረት።

***ማጠ**

ምጥ ስ 1. ለመውለድ የደረሰች እንስት በመውለጃዋ ሰአት ልጁ ከማህፀኗ እንዲወጣ የምታደርገው ወደ ታች የመጫን፥ የመግፋትና እህ የማለት ጥረት። 2. (ዘይ.) ጭንቀት፥ ጥበት።

አማጠ ግ 1.ከሆዱ ውስጥ ወደ ውጭ ገፋ፥ እህ አለ (አይነምድርን)። 2. (ዘይ.) ተጨነቀ፥ ተጠበበ።

አማጠች እርጉዝ በወሊድ ጊዜ ልጇን ከማህፀኗ ለማስወጣት ወደታች ገፋች፥ እህ አለች።

አሰማጠ ግ ላልወጣም በማለት በጣም እህ አሰኘ፥ አስጨነቀ (አይነምድር)።

ማጠቃለያ "ጠቀለለ" ስር ተመ.

ማጠናከሪያ "ጠነከረ"ስር ተመ.

ማጠንት "አጠነ" ስር "ማእጠንት"ን ተመ.

ማጠንፈፊያ "ጠነፈፈ" ስር ተመ.

ማጠፊያ "አጠፈ"ስር ተመ.

ማጣሪያ "ጠራ^{2}" ስር ተመ.

ማጣበቂያ "*ጠበቀ" ስር ተመ.

ማጣፈጫ "ጣፈጠ" ስር ተመ.

ማጣፊያ "አጣፋ" ስር ተመ.

ማጥ ስ አረንቋ፥ ረግረግ።

ማጥለያ "ጠለለ" ስር ተመ.

ማጨሻ "ጨሰ" ስር ተመ.

ማጩራ ስ በሽንብራ እሸት ቅጠልና በፍሬው ሽፋን ላይ የሚገኝ ጨው ጨው የሚል ወዝ።

ማጫ "አጨ" ስር ተመ.

ማጫወቻ "*ጫወተ" ስር ተመ.

ማጫጫሻ "ጨሰ" ስር ተመ.

ማጭዴ ስ የቁጥኝ በሽታ አይነት።

ማጭድ "አጨደ" ስር ተመ.

*ማፀነ

ተማፀነ (ተማጠነ) ግ አጥብቆ ለመነ፥ ተማለዱኝ አለ።

አማፀነ (አማጠነ) ግ 1. ለሌላ ለመነ፥ አማለደ። 2. ተማፀነ።

ማፅናኛ "ጠና" ስር ተመ.

ማፈሪያ "አፈረ" ስር ተመ.

ማፈኛ "አፈነ" ስር ተመ.

ማፉጻ ስ ከቆዳ የተሰራ ከረጅ፥ ከረጢት፥ ቦርሳ።

ማሟያ "ሞላ" ስር ተመ.

ሜ ቅ "መ" ፊደል ሃምስ ዘር።

ሜል ስ የሰባ በሬ፥ ሰንጋ።

ሜርቆ (መርቄ) ስ በወይናደጋ አካባቢ የሚበቅል ሰይፍ የሚመስል ረዣዥም ቅጠል ያለው ዛፍ።

ሜርኩሪ^{1} ስ ፈሳሽ የሆነና ብርማ ነጭ መልክ ያለው ማእድን፤ ባዙቃ።

ሜርኩሪ^{2} ስ ለፀሃይ ቅርብ ሆና የምትገኘና ፀሃይን ከሚዞሩት ዘጠኝ ፕላኔቶች አንዷ ፕላኔት (በተጨማሪ ፕላኔት ስር ተመ.)።

ሜሮን ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) አዲስ አባል ክርስትና ሲነሳ፥ ካህን ሲሾም፥ ንጉስ ሲነግስ፥... በካህናት እጅ የሚቀባው ቅባት፤ ቅብአ ቅዱስ።

ሜትር "መተረ^{1}" ስር ተመ.

ሜንዶ "መንደ"ን ተመ.

ሜንጦ ስ ስጋን ወይም ልዩ ልዩ እቃዎችን እንዲያንጠለጥል ሆኖ የተሠራ ቆላፋ ብረት፥ እንጨት፥... ወይም በግንድ ጫፍ ላይ የበቀሉ በርካታ የባላ ጣቶች ያሉት የእንጨት መስቀያ።



ሜንጦ

ሜካኒክ "መካኒክ"ን ተመ.

ሜዳ ስ 1. ዳገት ቁልቁለት፥ ጫካ የሌለው ሰጥ ያለ ሰፊ መሬት። 2. ከቤት ውጪ፥ የትም ቦታ። *የጠፋው ሰአት ሜዳ ላይ ወድቆ ተገኘ።*

ሜዳ ሙሉ ብዙ፥ አያሌ።

ሜዳ ወጣ ሜዳ ላይ፥ ጫካ ውስጥ ተፀዳዳ።

ሜዳ ወጣች ጉያዋን፥ ብልቷን ታጠበች፤ የገብር ውሃ ወጣች፤ ተፀዳዳች።

የሜዳ አህያ ስ መላ አካሉ በነጭና ጠቆር ባለ የቀለም ሰብጥር የተሸለመለመ፥ ቁመቱ ከአህያ ከፍ የሚል የዱር እንስሳ።(ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።

የሜዳ ፍየል ስ ረገዥም ቀንዶች ያሉትና ፍየል የሚመስል የዱር እንስሳ(ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።

ሜዳይ (ሜዳሊያ) ስ ከወርቅ ወይም ከብር ወይም ከነሃስ፥... የተሰራ፥ በተለያዩ የሙያ መስኮች ወይም ውድድሮች ብልጫ ላሳዩ ወይም ጥሩ ለሰሩ ሰዎች ከመንግስት፥ ከድርጅት፥... የሚሰጥ ሽልማት፤ ኒሻን።

ሜጀር ጄኔራል ስ ከብርጋዴየርና ሌፍቴናንት ጄኔራል መሃል የሆነ ወታደራዊ ማእረግ።

ም ቅ "መ" ፊደል ሳድስ ዘር።

_ም 1. እንዲሁም፥ በተጨማሪ። *ደብተር ብቻ ሳይሆን እርሳስም ገዛሁ።* 2. ሌላው ቀርቶ፤ እንኳን። *በስብሰባው ላይ አንድም ሰው አልተገኘም።*

ምሁር "መሃረ" ስር ተመ.

ምህላ ስ ፀሎት፥ ምልጃ፥ ልመና።

ምህረት "ማረ" ስር ተመ.

ምህንድስና "መሃንዲስ" ስር ተመ.

ምህዋር ስ መዞሪያ፥ መሄጃ መስመር (የፕላኔቶች)።

ምህፃረ ቃል ስ በሙሉ ቃል ፋንታ በአጭሩ የሚፃፍ፤ የሚነገር ቃል (ለምሳሌ ወዘተርፈ በማለት ፈንታ ወዘተ.)።

ምላስ "ላሰ" ስር ተመ.

ምላሽ "መለሰ" ስር ተመ.

ምላት "ሞላ" ስር ተመ.

ምላጭ "ላጨ" ስር ተመ.

ምልመላ "መለመለ^{2}" ስር ተመ.

ምልማይ "መለመለ^{1}" ስር ተመ.

ምልምል^{1} ዝ.ክ.

ምልምል^{2} "መለመለ^{2}" ስር ተመ.

ምልሰት "መለሰ" ስር ተመ.

ምልስ ዝ.ክ.

ምልአተ ጉባኤ "ሞላ^{1}"ስር ተመ.

ምልአት ዝ.ክ.

ምልኩስና "መነኮሰ" ስር "ምንኩስና"ን ተመ.

ምልኪ "መለከ" ስር ተመ.

ምልክት "መለከተ"ስር ተመ.

ምልጃ "ማለደ^{2}" ስር ተመ.

ምረቃ "መረቀ" ስር ተመ.

ምሩቅ ዝ.ከ.

ምሪት "መራ" ስር ተመ.

ምራቅ ስ ከአፍ የሚወጣ አረፋነት ያለው ፈሳሽ ነገር።

ምራቁን ዋጠ ጎመጀ፥ ጓጓ።

ምራቁን የዋጠ በእድሜው የበሰለ፥ የሰከነ ሰው።

ምራት ስ የልጅ ሚስት።

ምራን "መረነ" ስር ተመ.

ምራጭ "መረጠ" ስር ተመ.

ምሬት "መረረ" ስር ተመ.

ምር ዝ.ከ.

ምርመራ "መረመረ" ስር ተመ.

ምርምር ዝ.ከ.

ምርቃት "መረቀ" ስር ተመ.

ምርቃና "መረቀነ" ስር ተመ.

ምርቅ ስ በሰንደ፥ በገብስ፥... እህል ፍሬ ጫፍ ላይ የሚገኝ እሾሃማ ጭገር።

ምርቅና ፍትፍት ጥሩና መጥፎ።

ምርታማ "መረተ^{1}" ስር ተመ.

ምርት ዝ.ከ.

ምርኩዝ "*መረኮዘ" ስር ተመ.

ምርኮ "ማረከ" ስር ተመ.

ምርኮኛ ዝ.ከ.

ምርጊት "መረገ" ስር ተመ.

ምርግ ዝ.ከ።

ምርጥ "መረጠ" ስር ተመ.

ምርጫ ዝ.ከ.

ምርፋቅ "ረፈቀ" ስር ተመ.

ምሰሶ (ምሶሶ) ስ 1. በገጠር አካባቢ በተለይ ክብ ቅርፅ ይዞ በሚሰራ የሳር ቤት ውስጥ፥ ከቤቱ ወለል መካከል ላይ ተተክሎ፥ ጣሪያውን ተሸክሞ የሚቆም፥ ቀጥ ያለ፥ ረዥምና ጠንካራ የሆነ ግንዲላ። 2. የኤሌክትሪክ፥ የስልክ፥... ሽቦ የሚታሰርበት ረዥምና ወፍራም እንጨት። 3. ለጣሪያ ወይም ለታዛ መደገፊያ ተብሎ በበረንዳ ወይም በቤት ውስጥ የሚተከል የእንጨት፥ የብረት ወይም የድንጋይ ቋሚ። 4. (ዘይ.) ዋንኛ፥ ድጋፍ፥ መሰረት። *ታላቅ ወንድማቸው የቤቱ ምሰሶ ነው።*

ምሳ ስ እኩለ ቀን ላይ የሚበላ ምግብ።

ምሳ ቋጠረ ለምሳ የሚሆነውን ምግብ በአገልግል ወይም በሰሃን፥... ያዘ።

ምሳሌ "መሰለ" ስር ተመ.

ምሳሌያዊ ንግግር ዝ.ከ.

ምሳር "ጠገራ^{2}" ን ተመ.

ምሳና "ብሳና" ን ተመ.

ምሳግ "መሰገ" ስር ተመ.

ምስ ስ 1. ለሰይጣን፥ ለዛር፥ ለቡዳ፥... የሚሰጥ ድርጎ፥ ግብር። 2. ቅጣት። *ምሱን አገኘ።*

ምስለቢስ "መበለ" ስር ተመ.

ምስሌኔ ስ በባላባቱ ስርአት የመሬት ስሪት ውስጥ መንግስት ወይም መልከኛ፥... የሚወክለው፥ ስልጣኑ ከጭቃ ሹም በላይ የነበረ ሹም።

ምስል "መሰለ" ስር ተመ.

ምስማር (ሚስማር) ስ በአንድ በኩል ሹል ጫፍ በሌላ በኩል ጠፍጣፋ ራስ ያለው፥ እንጨትና ቆርቆሮ የመሳሰሉትን ለማያያዝ የሚያገለግል ትንሽ የብረት ዘንግ።

ምስማር

ምስማክ^{1} "ሰበከ" ስር "ምስባክ" ን ተመ.

ምስማክ^{2} ስ በመፅሃፍ ገፆች መጋጠሚያ ግራና ቀኝ ላይ ያለ ባዶ ቦታ።

ምስረታ "መሰረተ" ስር ተመ.

ምስራቅ ስ ከአራቱ ማእዘናት አንዱ የሆነና በፀሃይ መውጫ በኩል ያለ አቅጣጫ፤ የምእራብ ትይዩ።

ምስራቃዊ ቅ 1. በስተምስራቅ አቅጣጫ ያለ፥ የሚገኝ። 2. የምስራቅ።

ምስራች ስ የደስታ ወሬ፥ ዜና።

የምስራች 1. አንድን የደስታ ወሬ ለመጀመሪያ ጊዜ ለመናገር ወይም ለማብሰር እንደመግቢያ ወይም እንደመንደርደሪያ ሆኖ የሚነገር ቃል (ለምሳሌ ተናጋሪ "የምስራች" ሲል ሰሚ "ምስር ብላ" ብሎ ይመልሳል)። 2. እንደ ቡና፥ ብርቱካን፥ ወይን፥ ትርንጎ፥... ያለ ተክል ለመጀመሪያ ጊዜ የሚያፈራው ፍሬ። *ቡናው የምስራች ሰጠ።*

ምስር ስ ከአተር በመጠን የሚያንስ፥ ጠፍጣፋና ክብ የሆነ፥ ለወጥ፥ ለንፍሮ፥... የሚሆን ከጥራጥሬ እህሎች አንዱ፤ ፍሬውን የሚያፈራው ተክልም ምስር ይባላል።

ምስር ብላ የደስታ ወሬ ለመንገር "የምስራች" ላለ ሰው የሚሰጥ ምላሽ።

ምስር ጥርስ ስ 1. የወተት ጥርስ። 2. በጣም ትንንሽ የሆነ ጥርስ።

ምስሬ ስ የቂጥኝ አይነት።

ምስርቃና (ምስረቃና) ስ እምቢልታ ወይም መለከት።

ምስርች ስ ቅጠሉ እንደምስር ቅጠል ያለ ሆኖ እንጨቱ መሰል ብሉ ረዘም ያሉና ለጨፈቃነት የሚያገለግል የእፅዋት አይነት።

ምስቅልቅል "*መሰቀለ" ስር ተመ.

ምስባክ "ሰበከ" ስር ተመ.

ምስኪን ቅ 1. ያጣ የነጣ፣ ጠም አዳሪ፣ የተቸገረ ደሃ። 2. አሳዛኝ (ሰው፣ እንስሳ፣...)። 3. የዋሀ።

ምስክር "መሰከረ" ስር ተመ.

ምስያ "መሰለ" ስር ተመ.

ምስጉን "*መሰገነ" ስር ተመ.

ምስጋና ዝ.ከ.

ምስጋን የለሽ ዝ.ከ.

ምስጢረ ስላሴ "*መሰጠረ" ስር ተመ.

ምስጢረ ስጋዌ ዝ.ከ.

ምስጢረኛ ዝ.ከ.

ምስጢር ዝ.ከ.

ምስጥ ስ 1. እንጨትን እየበላና እየሰረሰረ የሚገባ፣ በመሬት ውስጥ ለውስጥ መሄድ የሚችል፣ ቅርፁ ጉንዳን የሚመስል ቀይ ነፍሳት። 2. (ዘይ.፣ ስድብ) ማንም ሳያውቅበት አንድን ነገር ውስጥ ለውስጥ የሚፈፅም፣ ማሽንክ።



ምስጥ 1ኛ ፍቺ

ምሶሶ "ምሰሶ"ን ተመ.

ምሽሽ ስ ከስንደዶና ከአክርማ የሚሰራ የእህል መስፈሪያ፣ ሳጻን።

ምሽሮ (ሙሽሮ) ስ ካንገት ላይ የሚወጣ፣ ቶሎ የማይሽር ቁስል፣ ነቀርሳ።

ምሽት "ሚስት"ን ተመ.

ምሽት "መሸ" ስር ተመ.

ምሽግ "መሸገ" ስር ተመ.

ምቀኛ "*መቀኘ" ስር ተመ.

ምት "መታ^{1}" ስር ተመ.

ምትሃት (ምታት) ስ ድግምት፣ አስማት ወይም ሌሎች ነገሮችን በማድረግ በአይን ብቻ ሲታይ የሚቻል አስገራሚ ድርጊት ሆኖ ነገር ግን ወዲያው የሚጠፋ ወይም እውነትነት የሌለውና የማይጨበጥ ነገር።

ምትሃተኛ ቅ ምትሃት የማድረግ ወይም የመስራት ችሎታ ያለው (ሰው)።

ምትክ "ተካ" ስር ተመ.

ምቹ "*መቸ" ስር ተመ.

ምች "መታ" ስር ተመ.

ምቾት "*መቸ" ስር ተመ.

ምነና "መነነ" ስር "ምናኔ"ን ተመ.

ምናሄ (መናሄ) ስ ለመድሃኒትነት ያገለግላል የሚባል፣ ቅርፊቱ ነጭ የሆነና በቆላ የሚበቅል አነስተኛ ዛፍ።

ምናልባት "ምን" ስር "ምንአልባት"ን ተመ.

ምናምን "ምን" ስር ተመ.

ምናምንቴ ቅ የማይረባ፣ ተልካሻ፣ ልክስክስ።

ምናኔ "መነነ" ስር ተመ.

ምኔት ስ ገዳም።

አበምኔት ስ የወንዶች ገዳም አለቃ፣ ሹም ወይም አስተዳዳሪ።

እመምኔት ስ የሴቶች ገዳም ሹም ወይም አስተዳዳሪ (መነኩሲት)።

ምን (ምንድን፣ ምንድር) ተው.ስ. 1. ያልታወቀን ነገር ማንነት፣ ምንነት፣ አይነት፣... ለማወቅ ሲፈለግ ጥያቄ ማቅረቢያ ሆኖ የሚያገለግል ቃል። *ሀ. የምታነበው ምን መፅሃፍ ነው? ለ. ምን እየሰራህ ነው?* 2. በጣም፣ የትኛውንም ያህል። *መንገዱ ምን ቢርቅ ከሁለት ሰአት በላይ አያስኬድም።*

ምነው ለምን፣ በምን ምክንያት። *ምነው ቀረህ።*

ምኑ ቅጡ ብዛትን በማጋነን ለመግለፅ የሚያገለግል ቃል። *የልብሱ፣ የወርቁ ፣ እሩ ምኑ ቅጡ!*

ምኑ ነች 1. ያላቸው ግንኙነት፣ ዝምድና እንዴት ነው? 2. አትበቃውም፣ ታንሰዋለች፣ ቅምም አትለው። *ለምስት እንጀራ ለሱ ምኑ ነች።*

ምኑንም ምኑንም የተገኘውን ሁሉ (ሳይመርጥ)።

ምን ሆነ ምን አጋጠመው፣ ምን ነካው።

ምን መሆን ነው 1. ምንድን ነው፣ *ይሄ እቃ ምን መሆን ነው?* 2. ምን ማድረግ ነው? *ምን መሆን ነው ስራውን ትቶ የሄደው?*

ምን መጣ 1. የመጣው ምንድነው? 2.

በምን ምክንያት (የእምቢታ አገላለፅ)።

ምንመጣብኝ እንዴት አይነት መጥፎ ነገር ገጠመኝ!

ምን ቆርጦኝ 1. በምን ምክንያት (አላደርገውም፣ ምን በወጣኝ የማለት የእምቢታ መልስ)። 2. ምን አስገድዶኝ፣ ምንአግብቶኝ።

ምን በሳው የት ሄደ፣ የት ደረሰ።

ምን በወጣኝ ምን ባደረግሁ፣ ምን ባጠፋሁ፣ በምን ምክንያት፣ ለምን።

ምንቤት ነህ ምን አገባህ፤ ምን ጥልቅ አደረገህ።

ምንተጻዬ ምንቸገረኝ፤ ግድ የለኝም።

ምንቸገረኝ 1. ምን አገባኝ። 2. ግዴለኝም፣ ይሁን፤ እሺ።

ምንአለበት (ምናለበት) ምን ይጎዳል፣ ምን ያስቸግራል (አይጎዳም፣ አያስቸግርም፣ ይሁን ለማለት የሚነገር)።

ምንአልባት የግምት፣ የጥርጣሬ፣ የይሆን ይሆናል አነጋገር። *ምናልባት እመጣ ይሆናል።*

ምንአባቱ(ምናባቱ) 1. የስድብ ቃል። 2. የተስፋ መቁረጥ፣ የንዴት፣... መግለጫ ቃል። *ምናባቱ ቢቀርስ! ምናባቱ ላድርግ።* 3. የፍርሃትና የአክብሮት መግለጫ ቃል። *ምናባቱ ቆርጦኝ ነው እሱን የምናገረው!*

ምንአውቄ (ምናውቄ) እኔ አላውቅም፣ እኔ እጃ።

ምንአውቅልህ (ምናውቅልህ) በእንቆቅልሽ ጥያቄ ጊዜ ተጠያቂው ለመልስ መዘጋጀቱን ለመግለፅ የሚናገረው ቃል (ለምሳሌ ጠያቂ "እንቆቅልህ" ሲል መላሽ "ምን አውቅልህ" ይላል። ትርጉሙ "ምን ልወቅልህ" ማለት ነው)።

ምንአገባኝ (ምናገባኝ) ምንቸገረኝ፣ ጉዳዩ አይመለከተኝም።

ምንከፋኝ እሺ፣ ይሁን፣ እንደተባለው ይፈፀም፣ ይደረግ።

ምንወሰደው የት ጠፋ፣ የት ነው ያለው፣ የት ሄደ።

ምን ዋጠው ዝ.ከ.

ምን ያህል ስንት።

ምን ይሆናል 1. ምን ይጠቅማል፣ ምን ያገለግላል። 2. የፀፀት ስሜትን ለመግለፅ የሚያገለግል አባባል። *ምን ይሆናል አሁን ሁሉም አለፈ!*

ምንገዶኝ 1. ምንቸገረኝ። 2. ለምን እምቢ እላለሁ።

ምንጊዜ (ምንዜ፣ ምንዬ፣ምኔ) መቼ፣ በየትኛው ጊዜ፣ በስንት ሰአት።

[ለ] ምንጊዜም 1. ሁልጊዜ። 2. በማንኛውም ጊዜ።

ምን ጥልቅ አደረገህ ምን አገባህ።

ከምንጊዜው (ከምኔው) ከመቼው፣ እንዴት ባለ ፍጥነት።

ምንና ምን የትና የት፣ ወዲትና ወዲት፣ ሩቅ ለሩቅ፣ የማይገናኝ፣ የማይወዳደር፣ የማይመሳሰል። *ዝሆንና ትንኝ ምንና ምን ናቸው።*

እንደምን ነህ ጤንነትህ፣ ኑሮህ፣ በምን አይነት ሁኔታ ላይ ነው ለማለት የሚነገር የሰላምታ ቃል።

ምንነት የአንድ ነገር (ባህሪ፣ አመጣጥ፣ ተፈጥሮ፣...) መታወቂያ፣ መለያ።

ምንኛ በጣም፣ በሃይል። *ምንኛ ከብሯል!*

ምናምን የሆነ ነገር፣ አንድ ነገር።

ምናምን በለኝ አንድ ነገር ጋብዘኝ፣ ስጠኝ።

ምናምኒት አንድም ነገር፣ ሳምል ታህል እንኳን። *የሚበላ ምናምኒት የለኝም።*

ምንም ቅ ባዶ፣ አንድም፣ ትንሽም። *ምንም የለኝም።*

ምንም አይቀረው የማያደርገው ወይም የማይበላው ወይም የማይጠጣው፣... ነገር የለም።

ምንም አይቀራት ውብ ፣ ቆንጆ ናት።

ምንም አይወጣው 1. ምንም አይናገር። 2. እንከን አይገኝበትም።

ከምንም አይቆጥረው 1. ይንቀዋል፣ አይፈራውም። 2. አያስቸግረውም፤ አቅልሎ ይመለከተዋል።

ምንም ቢሆን የሆነው፣ የፈለገው ቢሆን።

ምንም አይል 1. ደህና ነው፤ መጠነኛ፣ መካከለኛ ነው። 2. አይጎዳም። 3. አይናገርም፣ አይቆጣም። *ልጁ ቢያመሽ አባቱ ምንም አይልም።*

ምንም አይደል ግዴለም፣ አያስጨንቅም፣ አያሳስብም።

ምንም [እንኳን] ቢሆንም ቅሉ።

በምንም አይነት ፈፅሞ፣ በጭራሽ፣ የፈለገው ቢሆን።

እንደምንም በተቻለ መጠን፣ በጥረት።

ምንሽር ስ የጠመንጃ ስም።

ምንሽንሽ "መነሽነሽ" ስር ተመ.

ምንሽ ስ ተቅማጥ።

ምንቂያም "*መነቀ" ስር ተመ.

ምንቃር "*ነቆረ" ስር የ"መንቆር"ን 1ኛ ፍቺ ተመ.

ምንቅ ምንቅ አለ "*መነቀ"ስር ተመ.

ምንባብ "*ነበበ" ስር ተመ.

ምንተ__ ስለ____። *ምንተማርያም*።

ምንተእፍረቱን ስላፈረ። *በሰዎች ፊት ስለጠየቅሁት ምንተእፍረቱን ገንዘቤን ሰጠኝ።*

ምንትስ የአንድ ነገር ስም ሲረሳ ወይም ስሙን ለመጥራት ባልተፈለገ ጊዜ በምትኩ እየገባ የሚያገለግል ቃል።

ምንቸት ስ ለወጥ መስሪያ፣ ለንፍሮ፣ ለጎመን፣... መቀቀያ የሚያገለግል የማሰሮ አይነት(ስእሉን የሸክላ እቃ ስር ተመ.)።

ምንቸት አብሽ ስ በጣም ደቆ ከተከተፈ ስጋ የሚዘጋጅ የወጥ አይነት።

ምንኩስና "**መነኮሰ**" ስር ተመ.

ምንዛሪ "**መነዘረ**" ስር ተመ.

ምንዝር "**መነዘረ**" ስር ተመ.

ምንዳ ስ የድካም ወይም የስራ ዋጋ፣ ደመወዝ።

ምንደኛ ቅ 1. ተቀጥሮ የሚሰራ፣ ደመወዝተኛ። ስ 2. ቅጥረኛ፣ ለገንዘብ የሚሰራ።

ምንድር "**ምን**" ን ተመ.

ምንዝላት (**ምዝላያት፣ ምንዥላት**) ስ የሸማት አባት ወይም እናት፣ 5ኛው አያት።

ምንጣፍ "***ነጠፈ**" ስር ተመ.

ምንጭ "**መነጨ**" ስር ተመ.

ምንጭር ስ የላይኛው ከንፈር (ብዙ ጊዜ ለከብት)።

ምንጭራም ቅ (ስድብ) የላይኛው ከንፈሩ ትልቅ የሆነ።

ምንጭርር ስ ስሩ ተቀጥቅጦ ለማቅለሚያነት የሚያገለግል እፅ።

ምኞት "***መኘ**" ስር ተመ.

ምእላድ ስ ትርጉም አዘል የሆነና አነስተኛ ወደ ሆነ ሌላ ትርጉም አዘል ክፍሎች ሊከፈል የማይችል የመጨረሻ ንኡስ አሃድ ወይም ክፍል (ለምሳሌ "ሆድ" ራሱን የቻለ ቃል ወይም ምእላድ ሲሆን "ሆዳም" ግን የ"ሆድ" እና የቅፅል መስሪያ "-ም" ጥምረት ማለትም የሁለት ምእላዶች ጥምረት የፈጠረው ቃል ነው)።

ምእመን "**አመነ**" ስር ተመ.

ምእራብ ስ ከአራቱ ማእዘናት አንዱ የሆነና በፀሃይ መጥለቂያ በኩል ያለ አቅጣጫ፤ የምስራቅ ትይዩ (በተጨማሪ ማእዘንን ተመ.)።

ምእራባዊ (ብ.ቁ. **ምእራባውያን**) ቅ 1. በምእራብ አቅጣጫ በኩል ያለ፣ የሚገኝ። 2. የምእራብ። ስ 3. (ለብዙ ቁጥር ሲሆን) የምእራብ አውሮፓና የሰሜን አሜሪካ አገሮች በአንድ ላይ የሚጠሩበት ስም።

ምእራፍ ስ 1. በመፅሃፍ ውስጥ ያለ የመፅሃፉ መከፈያ (ብዙውን ጊዜ በቁጥር ይጠራል፤ ለምሳሌ ምእራፍ አንድ፣ ምእራፍ ሁለት)። 2. በረዥም የቦታ ርቀት መሃል የሚገኝ የተወሰነ አሜጭር የቦታ ርቀት። 3. (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ወደ ቀብር ቦታ የሚጓዝ ሬሳን በየመንገዱ እያሳረፉ የጉዞ ፍታት ወይም ፀሎት የሚያደርጉበት ስፍራ። 4. አንድ ክንዋኔ ወይም ሁኔታ አልፎ ሌላ የሚጀመርበት ወቅት። *በኢኮኖሚ እድገት አዲስ ምእራፍ ጀምረናል።*

ምእዙን "**ማእዘን**" ስር ተመ.

ምኩራብ ስ 1. የአይሁድ ፀሎት ቤት። 2. (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) የሁዳዴ ፆም ሶስተኛው ሳምንት።

ምክር "**መከረ**" ስር ተመ

ምክትል "***ከተለ**" ስር ተመ.

ምክቶሽ "**መከተ**" ስር ተመ.

ምክንያት "***መከኘ**" ስር ተመ.

ምክክር "**መከረ**" ስር ተመ.

ምዝላያት "**ምንዝላት**" ን ተመ.

ምዝራጥ (**ምዥራጥ**) ስ ትልቅ አንካሴ፣ ሽብዳ።

ምዝበራ "**መዘበረ**" ስር ተመ.

ምዝብር ዝ.ከ.

ምዝገባ "**መዘገበ**" ስር ተመ.

ምዥራጥ "**ምዝራጥ**"ን ተመ.

ምድማድ "**መደመደ**" ስር ተመ.

ምድር ስ መሬት።

ምድር ሰማይ ዞረበት 1. ነገሩ ሁሉ ተሳከረበት፣ ተምታታበት፣ መለየት አቃተው። 2. በበሽታ ወይም ከመጠን በላይ የሚያሰክር መጠጥ በመጠጣቱ ሰማዩም ምድሩም፣ በአካባቢው ያለው ነገር ሁሉ የሚሽከረከር፣ የሚገለባበጥ መሰለው።

ምድር ቀለጠች በደስታ፣ በፈንጠዝያ፣ በጨዋታ ወይም በጠብና በጦርነት ምክንያት ትርምስ፣ ድብልቅልቅ ሆነ።

ምድር አለፈ (አለፈች) ዝ.ከ.

ምድር ከዳችው ድንገት ሳያስበው ወደቀ (አዙሮት፣ አዳልጦት ወይም አንሸራትቶት)።

ምድር ፊት አስቀያሚ።

ከምድር ተነስቶ ያለምንም ምክንያት።

ምድረ__ __ሁሉ፣ ማንም፣ አንድም ሳይቀር። *ምድረ ኩታራ ተሰብስቦ ሊንጫጫ የለ።*

ምድረ በዳ (በዳ) ስ 1. እፅዋትና ውሃ የማይገኝበት ደረቅ ቦታ፣ በረሃ። 2. ሰው የማይኖርበት ጭር ያለ ቦታ፣ አካባቢ።

ከምድረ ገፅ (ከገፀ ምድር) ከምድር ላይ።

በአሁኑ ጊዜ ፈንጣጣ ከምድረ ገፅ ጠፍቷል።

ምድር ቤት ስ ፎቅ ሆኖ በተሰራ ቤት ውስጥ ከመሰረቱ በላይና ከአንደኛው ፎቅ ስር ያለው ቤት።

የምድር ሰላጤ ስ ከሚፉ ሾልና ሾጠጥ ብሎ ወደባህር የሚገባ የመሬት አካል፣ ጠርዝ።

የምድር ሰቅ/ወገብ ስ በምስራቅና በምእራብ አቅጣጫ በምድር ወገብ ዙሪያ የተሰመረ የሃሳብ መስመር።

የምድር በርበሬ ስ ወደ ቅላት የሚያደላ ቢጫ አበባ ያለው፣ እንጥል ሲወርድ መድሃኒት ነው ተብሎ የሚበላ፣ የሚያቃጥል የእፅዋት አይነት።

የምድር እንቧይ ስ ቅጠሉና የፍሬው ሽፋን ጭገራም የሆነ፣ ሲበስል ቀይ የሚሆን፣ ኮክ የሚያክል ፍሬ ያለውና መሬት ላይ የሚተኛ አነስተኛ ሃረግማ የእፅዋት አይነት።

የምድር ዋልታ ስ የምድር ሰሜናዊ ወይም ደቡባዊ ጫፍ።

የምድር ዝላይ ስ (ስፖ.) ከአንድ ከተወሰነ መነሻ ቦታ ላይ ተነስቶ በአየር ላይ አግድም በመወርወር የሚደረግ ዝላይ።

የምድር ጉድ በጣም አጭር፣ ድንክ።

የምድር ጦር ስ እግረኛን፣ ታንከኛን፣ መድፈኛን፣... የሚያጠቃልል በመሬት ላይ እየተጓዘ የሚዋጋ ወታደራዊ ክፍል።

ምድራዊ (ብ.ቁ. **ምድራውያን**) ቅ 1. አለማዊ፣ ስጋዊ፣ መንፈሳዊ ያልሆነ። 2. በምድር ላይ ያለ፣ የሚገኝ፣ የሚኖር (ፍጡር)።

ምድብ "**መደበ**" ስር ተመ.

ምድጃ "**ነደደ**^{1}" ስር ተመ.

ምግባር "***ገበረ**^{1}" ስር ተመ.

ምግብ "**መገበ**" ስር ተመ.

ምጎጎ (**ሙጎጎ**) ስ ከሸክላ የሚሰራ የእንጀራ መጋገሪያ ምጣድ።

ምጣት "**መጣ**" ስር ተመ.

ምጣኔ "**መጠነ**" ስር ተመ.

ምጣድ "**ጣደ**" ስር ተመ.

ምጣጭ "**መጠጠ**" ስር ተመ.

ምጥ "***ማጠ**" ስር ተመ.

ምጥማቅ "**ጠመቀ**^{2}"ስር ተመ.

ምጥማጥ (**ሽለምጥማጥ**) ስ 1. መጠኑ ድመት የሚያክል፣ ጅራቱ ረዥምና እግረ አጭር የሆነ አውሬ። 2. (ዘይ.፣ ስድብ) በጣም ጥቁር (ለመልክ)።(ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።

ምጥቀት "**መጠቀ**" ስር ተመ.

ምጥን "**መጠነ**" ስር ተመ.

ምፀት ስ በቀጥታ የቀረበውን ወይም የተነገረውን ሃሳብ ትርጉም ተቃራኒ የሚያሳይ የንግግር ስልት፣ የዘይቤያዊ አነጋገር አይነት።

ምፅአት ስ በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ ክርስቶስ ለሁለተኛ ጊዜ ወደ አለም የሚመጣበት ጊዜ።

ምፅዋት "**መፀወተ**" ስር ተመ.

ሞ የ"**መ**" ፊደል ሳብእ ዘር።

ሞሆዶ "**መሆዶ**" ን ተመ.

ሞለለ ግ የክብነት ቅርፅ ይዞ ቁመቱ ረዘመ፣ ሞላላ ሆነ።

ሞላላ ቅ ቅርፁ ክብ ሆኖ ቁመቱ ረዘም ያለ።

ሞለሞለ ግ ሾጠጠ፣ ሞለል አለ።

ሙልሙል ስ ሞለል ያለ ሀብስት፣ ጢቢኛ (ብዙውን ጊዜ ለቡሄ በአል የሚዘጋጅ)።

አሞለሞለ ግ 1. ሙልሙል ጋገረ። 2. ሞላላ አደረገ። 3. አበጠ፤ አሞጠሞጠ (ለምሳሌ ለመፍረጥ የደረሰ ብጉንጅ፣ እባጭ፣...)።

ሞለሰሰ ግ 1. በብዛት ነጨ፣ ነቀለ፣ መዘዘ። 2. አስተኛ፣ አጋደመ፣ ለጠሰ።

ሞለቀቀ ግ 1. ፈለቀቀ፣ ከፋተ። 2. ገፈፈ፣ ገሸለጠ።

***ሞለቀቀ**

ሞልቃቃ ቅ ስርአት የሌለው፣ ቀበጥ።

ተሞላቀቀ ግ 1. ተንቀባረረ፣ ተንደላቀቀ፣ ተቀማጠለ። 2. ስርአት አጣ፣ ቀበጠ።

አሞላቀቀ ግ 1. አንቀባረረ፣ አቀማጠለ። 2. አባለገ፣ ስነስርአት የለሽ አደረገ።

ሞለገገ ግ ቂለ፣ ጀለ።

ሞለገግ (**ሞልጋጋ**) ቅ ቂል፣ ጅል።

ሞለጨ ግ 1. ምንም ሳያስቀር ጠራርጎ ወሰደ፣ ሟጠጠ፣ ባዶ አደረገ። 2. ሰረቀ። 3. ገረፈ፣ ቀጣ (እንደ አለንጋ፣ ጅራፍ፣ አርጩሜ ባለ)። 4. በጣም ተሳደበ።

ሙልጩን (**ሙልጭ**) **ሄደ** 1. ባዶ እጁን ቀረ፣ ምንም አጣ፣ ከሰረ። 2. ምንም ሳያገኝ፣ ምንም ሳይደርሰው ባዶውን ተሰናበተ፣ ወጣ።

ሙልጩን (**ሙልጭ**)**ወጣ** ዝ.ክ.

ሞላጫ ቅ 1. ወስላታ፣ የወጣለት ሌባ። 2. የማይያዝ፣ የማይጨበጥ።

ሙልጭ አለ ግ 1. ሙጥጥ አለ፣ ጥርግ አለ። *አንድም ሳይቀር ሁሉም ሙልጭ ብሎ ሄደ።* 2. ጥርት አለ፣ በደንብ ፀዳ። *ዕቃው ሙልጭ ብሎ ታጥቧል።*

ሙልጭ አደረገ ግ 1. ሟጠጠ፣ ባዶ

አደረገ፥ ምንም ሳይተው ቀረ። *ዕቃውን ሙልጭ አድርጎ ወሰደ።* 2. በጣም ተሳደበ። *ሴትዮዋን ሙልጭ አደረጋት።*

***ሞለጨለጨ**

ሙልጭልጭ ቅ ዳባጣ፥ ማላጋ፤ የማይጨበጥ።

ሙልጭልጭ አለ ግ ተሙለጨለጨ።

ሙልጭልጭ አደረገ ግ አሙለጨለጨ።

ተሙለጨለጨ ግ 1. አልያዝ፥ አልጨበጥ አለ። 2. ማላጋ ሆነ፥ ዳባጣ ሆነ።

አሙለጨለጨ ዝ.ከ.

***ሞለፈጠ**

ሞልፋጣ ቅ 1. ስራ ፈት፥ ዋልጌ፥ ማጋጣ። 2. ባለጌ፥ ዘልዛላ። 3. በአነጋገሩ፣ በአለባበሱ ወይም በሌላ ሁኔታው ደስ የማያሰኝ።

ተሞላፈጠ ግ 1. ስራ ፈታ፥ ዋልጌ ሆነ። 2. ባለገ፥ ተንዘላዘለ።

አሞላፈጠ ግ አሞላቀቀ፥ አንዘላዘለ።

ሞላ^{1} ግ 1. ባዶ ወይም ጎደሎ በነበረ ነገር ውስጥ ከላይ እስከ ገደፉ ጨመረ፥ ከተተ፥ ጢም አደረገ። 2 ቀዳ፣ ጨመረ። *ቤንዚን ሞላ።* 3. በአነሰው ወይም በጎደለው ላይ ጨምሮ ወይም አክሎ ልክ አደረሰ፥ በቂ አደረገ። 4. አደረገ፥ ፈፀመ፣ አሳካ። *ፎርሙን ሞላ።* 5. በማዞር፥ በመጠምዘዝ ወይም በሌላ መንገድ አስፈላጊውን ሃይል ሰጠ፥ እንዲሰራ አደረገ። *ሰዓቱን ሞላ።* 6. በተዘጋጀው የመጠይቅ ወረቀት ወይም ባዶ ቦታ ላይ አስፈላጊውን መረጃ ፃፈ። 7. ሊይዝ የሚችለውን ያህል ያዘ፥ ሙሉ ሆነ። *አዳራሹ ሞልቷል፥ ከዚህ በላይ ሰው አይጨምርም።* 8. ተሳካ፥ ተፈፀመ። *ሃሳቤ ሞላ።* 9. ሆነ። *ስድስት ሰዓት ሞላ።* 10. በዛ፥ አያሌ ሆነ። *ቡና ቤት በከተማው ሞላ።* 11. ያለውን ቦታ ሁሉ ያዘ። *ሜዳውን የሞላው ቆሻሻ ነው።*

በሞላ ሁሉም፥ በጠቅላላ።

ሞልቶታል ብዙ አለው። *ገንዘብ ሞልቶታል።*

ሞላለት ተሳካለት።

ከሞላ ጎደል ሙሉ በሙሉ ሳይሆን፥ በአብዛኛው።

መሙያ (መሙሊያ) ስ 1. የሰአት ሃይል መስጫና ማስተካከያ እጀታ። 2. አረፍተ ነገርን ሙሉ ማድረጊያ ቃል ወይም ሃረግ (ለምሳሌ *"ከመኪና ወደ ትምህርት ቤት ሄደ"* በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ "ወደ ትምህርት ቤት" የሚለው ሃረግ መሙያ ነው)።

ሙሉ ቅ ጢም ያለ፥ ያልጎደለ፥ ያልተቀነሰለት።

በሙሉ አይን አያየውም ከመሳሳት ወይም ከመፍራት ወይም ከንቀት ወይም ከጥላቻ የተነሳ አትኩሮ አይመለከተውም።

በሙሉ ልብ 1. በእርግጠኝነት። 2. በድፍረት።

በሙሉ አፍ በድፍረት።

ሙሉ ለሙሉ በጠቅላላ።

ሙሉ ልብስ ስ አንድ ላይ እንዲለበስ ሆኖ የተዘጋጀ አንድ አይነት ኮትና ሱሪ (የወንድ)።

ሙሉ ሰው ከወጣትነት ያለፈና በጣም ያልሸመገለ ሰው፣ ጎልማሳ።

ሙሉ ቀን ከጠዋት እስከ ማታ።

ሙሉ ቁጥር ስ ያለ ቀሪ ለሁለት መከፈል የሚችል ቁጥር (2፥4፥6፥...)።

ሙሉ ቃል ስ ምንም ሳይቀነስ ወይም ሳይጨመር እንዳለ የተወሰደ ንግግር።

ሙሉ በሙሉ በጠቅላላ።

ሙሉ ጨረቃ ስ ጨረቃ ሙሉ ክብ ሆና ስትወጣ የምትጠራበት ስም።

ሙሉ ፍታት ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ለፍታት ተብሎ ከተመደበው ፀሎት ውስጥ ምንም ሳይቀነስ ለሙታን የሚደረግ ፀሎት።

ባለሙሉ ስልጣን ለተሾመበት ቦታ ሙሉ ስልጣን ያለው።

ባለሙሉ ስልጣን አምባሳደር ስ በተመደበበት አገር-አገሩን በመወከል ማንኛውንም ጉዳይ የሚፈፅም አምባሳደር።

ምላት (ምልአት) ስ ሙሉነት።

ምልአተ ጉባኤ ስ አንድን ስብሰባ ለማካሄድ የሚያስችል ከተሰብሳቢዎች ውስጥ መገኘት ያለበትና በህግ ደንቡ ላይ የተደነገገ የአባላት ቁጥር ብዛት።

ተሞላ ግ 1. ተጥለቀለቀ፣ ተዋጠ። *በደስታ ተሞላ።* 2. ተላበሰ። *ፊቱ ፈገግታ ተሞላ።* 3. ተጠመደ፥ ተመረዘ። *ከልጅነቱ በተንኮል ተሞላ።*

ተሟላ ግ 1. ተፈላጊው ነገር ተገኘ፣ ቀረበ፥ ሙሉ ሆነ። 2. የታሰበው፥ የታለመው፥... ተሳካ፥ ተፈፀመ፥ ተደረገ።

አሟላ ግ የተፈለገውን ነገር አቀረበ፤ የጎደለውን አገኘ፤ ሙሉ አደረገ።

አሟልቶ የሰጠው እንከን የማይወጣለት፥ ምንም ያልጎደለው፥ ሁሉ ያለው።

ማሟያ ቅ የጎደለ ማስተካከያ።

ሞላ^{2} ስ ጥምዝ ሆኖ የተሰራ፥ ሲገፉ የመሰብሰብና ሲጎተት ደግሞ የመለጠጥ ባህሪ ያለው፣ ተገፍቶ ወይም ተጎትቶ ሲለቀቅ ወደፊተኛው ቅርፁ ወይም ቦታው መመለስ የሚችል ብረት ወይም ሽቦ።

ሞላጫ "ሞለጨ" ስር ተመ.

ሞልቃቃ “*ሞለቀቀ” ስር ተመ.

ሞልጋጋ “*ሞለገገ” ስር “ሞለገግ” ን ተመ.

ሞልፋጣ “*ሞለፈጠ” ስር ተመ.

ሞረሞረ^1 ግ ቦረቦረ፥ ሞሸለቀ፥ ውስጥ ውስጡ ተሰማ (ረሃብ)።

ሞረሞረ^2 ግ አሾለ፥ አሞጠሞጠ (አፍን)።

ሙርሙርት ቅ የሾለ፥ የሞጠሞጠ።

ሙርሙርት አፍ ቅ (ስድብ) ሹልአፍ፥ ሙጢ አፍ።

ሞረሽ ስ በጭለማ ወይም በአደጋ ጊዜ ከአካባቢው ራቅ ያለ ሰውን ለመጥራት የሚያገለግል የስም ምትክ (የሰውየው ስም የማይጠራው ሰውየውን ለአደጋ ላለማጋለጥ ሲባል ነው)።

ሞረደ ግ በሞረድ ፈገፈገ፥ ሳለ (ብረትን፥ ወርቅን፥ ጥፍርን፥...)።

ሞረዳይ ስ በሞረድነት የሚያገለግል በበረሃ ወይም በወንዝ ውስጥ የሚገኝ ሻካራ ድንጋይ።

ሞረድ ስ እንጨትን፥ ብረትን፥ ጥፍርን፥ ወርቅን፥... ለማለስለስ፥ ለማስላት፥ ለማሳነስ፥ ለማሳመር፥...የሚያገለግል ሻካራነት ያለው ብረት።

ሞራ ስ አብዛኛውን ጊዜ አንጀትና ጨጓራን ሸፍኖ፥ አንዳንዴም በጮማ ስጋ አካባቢ የሚገኝ ስብነት ያለው ነጭ የስጋ አይነት።

ሞራ ገላጭ ቅ ከብት ከታረደ በኋላ ወዲያውኑ ሞራውን ዘርግቶ በማየት የሚጠነቁል (ሰው)።

ሞራል ስ 1. የመንፈስ ብርታት፣ ጥንካሬ፥ ፅናት። 2. ግብረገብ።

የሞራል ካሳ ስ በስድብ፥ በመንገላታት ወይም በሌላ ምክንያት ለደረሰ በደል ወይም የክብር መነካት ለተበደለው የሚከፈል ካሳ።

የሞራል ድጋፍ ስ ለማበረታታት የሚሰጥ (ገንዘብ ወይም ቁሳቁስ ያልሆነ) የሃሳብ ድጋፍ።

ሞሸለቀ(መሸለቀ) ግ 1. ገሸለጠ፥ ገፈፈ፥ ላጠ። 2. ፈጀ፥ አቃጠለ፥ ላፈ። 3. ገረፈ፣ መታ (በጅራፍ፥በአለንጋ፥...)። 4. ሰረቀ። 5. ራበ፥ ሞረሞረ።

ሞሽላቃ ቅ ሌባ።

ተሞሻለቀ ግ አጭበረበረ።

ሞሸሞሸ ግ በመራስ ወይም በመበስበስ ሟሸሸ፥ ሉከሉከ።

ሞሸረ ግ 1. ሸፈነ፥ ጠቀለለ፥ ሸበለለ፥ በውስጥ አደረገ (ለምሳሌ የኮባ ተክል መሃል ለመሃል አዲስ የሚወጣውን ቅጠሉን)። 2. በአዲስ ልብስ፥ በጌጥ፥... አሳመረ፥ አስዋበ (ሙሽራን)። 3.በጫጉላ ቤት አስቀምጦ ጥሩ ጥሩ ነገር መገበ፥ ተከባከበ (ለምሳሌ ሙሽራን)።

ሙሽራ ስ 1. እንደ እንሰት፥ ሙዝና ዘንባባ ባሉ ተክሎች አናት ላይ አዲስ እየወጣ ያለውና የተጠቀለለው ወይም የተሸበለለው መሃከለኛው ቅጠል። 2. የጋብቻ በአሉን (ሏን) በማክበር ላይ ያለ(ች) ወይም በቅርቡ ያገባ (ች) እና በጫጉላ ቤት የሚገኝ ወይም የምትገኝ (ሰው)።

ሙሽሪት ስ ሴት ሙሽራ።

የሙሽራ ልብስ ስ ሴት ሙሽራ የሰርጓ እለት የምትለብሰው ልብስ፤ ቬሎ።

የሙሽራ ቤት ስ ጫጉላ ቤት።

ተሞሸረ ግ 1. ሙሽራ ሆነ። 2. አጌጠ፥ ተሸለመ (በሰርጉ እለት)። 3. ጫጉላ ቤት ገባ። 4.ተከተተ፤ ከቤት ሳይወጣ በድሎት፥ በከብካቤ ተያዘ፥ ተቀመጠ።

ሞሽላቃ “ሞሸለቀ” ስር ተመ.

ሞቀ ግ 1. ጋለ፥ ተኮሰ፣ ሰማ። 2. እሳት ላይ ትንሽ ቆየ፥ ለብ አለ፥ ሙቅ ሆነ። 3. ሙቀት ወሰደ፥ አገኘ። *እሳት ሞቀ*። 4. ወበቀ። 5. (ዘይ.) ደመቀ፥ ደራ (ጨዋታ፥ ወሬ፥...)።

ሞቀው የደስታ፣ የኩራት ስሜት ተሰማው።

የሞቀ 1. የደመቀ፥ ከፍ ያለ፥ ትልቅ። *የሞቀ አቀባበል*። 2. የተመቸ፥ የተደላደለ። *የሞቀ ትዳር*።

ሳይሞቅ ፈላ (ስድብ) ያለእድሜው የጉርምስና ባህርይ ወይም አድራጎት የሚያሳይ።

ሙቀት ስ 1. ግለት፥ ትኩሳት። 2. ወበቅ። 3. የቅዝቃዜ ተቃራኒ።

የሙቀት መለኪያ ስ የትኩሳትን መጠን ለመለካት የሚያስችል መሳሪያ፤ ቴርሞ ሜትር።

የሙቀት መለኪያ

ሙቅ ቅ 1. የሚሞቅ፥ የሚተኩስ። ስ 2. እንደ አጃ ወይም ስንዴ፥... ያለ የእህል ዱቄት፥ በተወሰነ መጠን ከውሃ ጋር ተበጥብጦና ተፈልቶ የሚጠጣ ፈሳሽ ምግብ፤ እንትክትክ ወይም አጥሚት። 3. ከእህል ዱቄት በተለይም ከስንዴ የሚዘጋጅና በማጣበቂያነት የሚያገለግል ወፈር ያለ ፈሳሽ።

ሞቃት ቅ የሚሞቅ (ወቅት፥ ስፍራ፥ አካባቢ፥...)።

ሞቅታ ስ መጠነኛ ስካር።

ሞቅ አለ ግ 1. ከሚገባው መጠን ትንሽ

አለፍ፡ በዛ አለ። *ወጡ ጨው ሞቅ ብሎታል።*

ሞቅ አለው 1. በመጠኑ ሰከረ። 2. ሞቀው።3. በአገኘው አስደሳች ሁኔታ የኩራት ስሜት ተሰማው።

ተሟሟቀ ን 1. ደራ፥ ደመቀ። 2. (ስፖ.) መጠነኛ የሰውነት እንቅስቃሴ አደረገ፤ ተፍታታ።

አሟሟቀ ን 1.(ዘይ.) አዳመቀ፥ አቃለጠ፥ ሆይ ሆይ አለ። 2. (ስፖ.) አፍታታ፥ አንቀሳቀሰ (ሰውነትን)።

አሟሟቂ ቅ ወሬ አዳማቂ፥ ሆይ ሆይ ባይ።

ሞቀሰለ ን ቁመቱ ረዘመ፥ ተንቀዋለለ።

ሞቀለል (ሞቅላላ) ቅ ረዥም፥ ቀውላላ።

ሞቀሞቀ ን 1. በደንብ ባለመብሰል ወይም በሌላ ምክንያት የተነሳ እንደሊጥ ሆነ (ዳቦ)። 2. በመቆየት፥ በመበስበስ ወይም በሙቀት የተነሳ ሉክሉክ (ፍራፍሬ)። 3. በሰበሰ፥ ሉክሉክ (ቁስል)።

አሞቀሞቀ ግ.ከ.

ሞቃት "ሞቀ" ስር ተመ.

ሞቅሳሳ “ሞቀሰለ” ስር ተመ.

ሞቅታ “ሞቀ" ስር ተመ.

ሞተ ን 1. ነፍሱ ከስጋው ተለየች፤ በህይወት መኖር አቆመ፥ በድን ሆነ። 2. ተዳከመ፥ ቀነሰ። *ገበያው ሞተ።* 3. ሃይሉ በጣም ተቀነሰ፥ አቅም አጣ። *ባትሪው ሞተ።* 4. ከመጠን በላይ ለፋ፥ ደከመ። *በስራ ብዛት ሞተ/ በሩጫ ሞተ።* 5. ቀነሰ፤ ጠፋ (ፍላጎት)። 6. የግብረ ስጋ ግንኙነት መፈፀም አቃተው (የወንድ አባለዘር)። 7. ሰነፈ ተስፋ ቆረጠ። *ልቡ ሞተ።* 8. አንድን ነገር ከተገቢው መጠን በላይ አደረገ። *በሳቅ ሞተ/ ሳልቅሶ ሞተ።*

ሞተላት 1. እጅግ በጣም ወደዳት፥ አፈቀራት። 2. ህይወቱን ሰዋላት።

የሞተ ተልካሻ፥ የማይረባ፤ ሃሞተ ቢስ።

የሞተ ነገር ያለቀለት።

ይሙት በቃ ስ የሞት ቅጣት፥ የሞት ፍርድ።

ሞተ ከዳ ስ 1. የሞተ ሰው በህይወት እያለ ይለብሰው የነበረና ለሌላ ሰው የተሰጠ ወይም የተሸጠ ልብስ፤ ነፍስ ይማር 2. ባለቤት የሌለው እቃ።

ሙት^{1} ቅ 1. የሞተ፥ በድን የሆነ። 2.(ዘይ.) በጣም ደካማ፥ ሃሞቱ የፈሰሰ። 3. እጅግ ከፍተኛ ፍቅር ያለው። *ለልጁ ሙት ናት።*

ሙት^{2} ቅ ለሁለተኛ መደብ ግለሰብ የተነገረውን ነገር እውነትነት ለማረጋገጥ የሚደረግ መሃላ (የተናገርኩት ነገር ሃሰት ከሆነ አንተን በሞት ልጣ እንደማለት ነው)። *ወንድሜ ሙት! ነገ እመጣለሁ።*

ለ___ ሙት ነው___ በጣም ይወዳል። *ለጓደኛ ሙት ነው/ ለገንዘብ ሙት ነው።*

ሙት አመት ስ የሟች አንደኛ አመት ወይም በየአመቱ ለሟች መታሰቢያ የሚደረግ ተዝካር።

የሙት ልጅ ስ አባቱ ወይም እናቱ ወይም ሁለቱም የሞቱበት ልጅ።

ሙትቻ ቅ ሰነፍ፥ ደካማ፥አቅመ ቢስ።

ሞት ስ የነፍስ ከስጋ መለየት፥ የህይወት ፍፃሜ፥ እልፈት።

ሞት ይርሳኝ እንደረሳሁህ እኔንም ሞት ይርሳኝ ለማለት ለጓደኛ፥ ለልጅ፥...የሚነገር የቀልድ አባባል።

በሞት ተለየ ሞተ።

የሞት ሞት ትልቅ ቅሌት፥ ውርደት።

የሞት ሞቱን ፍርሃት ወይም ድካም በተሞላው ከፍተኛ ጥረት፥ ትግል፤ እንደምንም።

የሞት ሽረት ትግል ወሳኝ ፍልሚያ፥ ለመጨረሻ የሚደረግ ከፍተኛ ትግል።

የሞት አፋፍ አደገኛ ሁኔታ፥ ለሞት የቀረበ።

የሞት ፍርድ ስ የሞት ቅጣት እንዲፈፀም የሚያደርግ ፍርድ።

ሟች ቅ 1. የሚሞት። *ሰው ሁሉ ሟች ነው።* ስ 2. የሞተ(ው) ሰው። *የሟች ቤተሰብ በተገኘበት...።*

ተሟሟተ ን ከፍተኛ ትግል ወይም ጥረት አደረገ፤ ተጋደለ።

አሞተ ን አደከመ፥ አሰነፈ። *አስቀድሞ ልቡን ስላሞተው ስራውን መስራት አቃተው።*

ሞተር ስ ነዳጅ በማቃጠል፥ የኤሌክትሪክ ሃይልን በመጠቀም ወይም በሌላ ሁኔታ ሃይል ሊፈጥር የሚችል ወይም አንድን መሳሪያ ሊያንቀሳቅስ የሚችል የመሳሪያው አካል።

ሞተር አጠፋ የሞተሩን እንቅስቃሴ አቆመ።

ሞተር ብስክሌት ስ በሞተር ሃይል የሚንቀሳቀስ ወይም የሚሽከረከር ብስክሌት፤ ዶቅዶቄ (ስእሉን መጓጓዣ ስር ተመ.)።

የሞተር ዘይት ስ የሞተርን መሽከርከር እንዲያቀላጥፍ ሞተር ውስጥ የሚጨመር ዘይት።

ሞተረኛ (ሞተር ብስክሌተኛ) ቅ ሞተር ብስክሌት በመጠቀም ስራውን የሚያከናውን።

ሞት “ሞተ”ስር ተመ.

*ሞነሞነ

ሞንሟና ቅ ያማረ፥ የተዋበ፥ ሽሙንሙን (ብዙውን ጊዜ ለሴት)።

ተሞናሞነ ን ተሽሞነሞነ፥ አማረ፥ ተዋበ።

አሞናሞነ ን አሽሞነሞነ፥ አሳመረ፥ አስዋበ።

***ሞነደለ**

ሞንዳላ ቅ ደልደል ያለና ያማረ (ብዙውን ጊዜ ለሴት የሰውነት ቅርፅ)፡

ተሞናደለ ግ ደልደል ብሎ ያማረ ሆነ (የሰውነት ቅርፅ)።

ተሞናደለች ግ ሞንዳላ ሴት የሰው አይን በሚስብ ሁኔታ ተራመደች።

አሞናደለ ግ እንዲመቸው፥ እንዲያምርበት አደረገ።

ሞነጨረ ግ 1. ቦጫጨረ፥ አበላሸ (ለፅህፈት)። 2.ቧጨረ።

ሙንጭርጭር ቅ የተበላሸ፥ የተቦጫጨረ፥ አስቀያሚ (ለምሳሌ ፅሁፍ፥...)።

ሞነጫጨረ ግ 1. ቦጫጨረ (ለምሳሌ ሰውነትን)። 2. ቦጫጨረ፥ የማይነበብ አድርጎ ወይም አበላሽቶ ፃፈ። 3. በጣም ያልታሰበበትና ያልተደከመበት፥ እንደ ነገሩ የሆነ ፅሁፍ አዘጋጀ።

ተሞነጫጨረ ግ 1. ተቦጫጨረ (ለምሳሌ ሰውነት)። 2. ተቦጫጨረ፥ ተበላሸ (ለፅህፈት)።

ሞንሟና "*ሞነሞነ"ስር ተመ.

ሞንዳላ "ሞነደለ"ስር ተመ.

ሞኖፖል ስ በአንድ የስራ መስክ በተለይ የተወሰነ ምርትን በማምረት፥ በመሸጥ፥... ረገድ ብቸኛ የሆነ ባለመብት ድርጅት። *ትንባሆ ሞኖፖል*።

በሞኖፖል ይዞታል ለብቻው ያለተቀናቃኝ ይዞታል።

***ሞኘ**

ሞኝ ቅ 1. ቂል፥ ጅል። 2. በቀላሉ የሚታለል፥ ተላላ። 3. የዋህ፥ ገር።

ሞኝ አንጓስ ስ እቤት የሚዘጋጅ አረቄ፣ ካቲካላ።

ሞኛሞኝ ቅ ሞኝነት ያለበት፥ ሞኝ ቢጤ፣ ቂላቂል።

ተሞኘ ግ ተታለለ፥ ተደለለ፥ ተሸነገለ።

አሞኘ ግ አታለለ፥ አቄለ፥ ሸነገለ።

ሞከረ ግ 1. አንድን ነገር ለማድረግ፥ ለመስራት፥ ለማወቅ፥... ጣረ ወይም ታገለ። 2. የአንድን ነገር ምንነት፥ በትክክል መስራትና አለመስራት ወይም መበላሸትና አለመበላሸት፥... ለማረጋገጥ ፈተሸ፥ ፈተነ፣ መረመረ። 3. በመጠኑ ቻለ። *መኪና መንዳት ይሞክራል*። 4. ቀመሰ፥ አየ። 5. ጀመረ። *ሞክሮ ተወው*። 6. ለካ፥ አጥልቆ አየ (ልብስን፥ ጫማን፥...)።

አይሞከርም 1. አይቻልም፥ ከባድ ነው። 2. አይደረግም።

ሙከራ ስ 1. አንድን ነገር ለመስራት ወይም ለማወቅ የሚደረግ ጥረት። 2. የአንድን ነገር ምንነት፥ መስራትና አለመስራት፥ መበላሸትና አለመበላሸት ለማወቅ የሚደረግ ምርመራ ወይም ፍተሻ። 3. የመጀመሪያ ልምምድ።

የሙከራ ጊዜ ስ አዲስ የተቀጠረ ሰራተኛ ቋሚ ከመሆኑ በፊት የጠባዩና የአሰራሩ ሁኔታ የሚገመገምበት ወቅት።

ተሞካከሩ ግ ተፈታተኑ፥ ተፈታተሹ (በጉልበት፥ በአቅም፥ በችሎታ)።

ተሞክሮ ስ ከተግባር፥ ከልምድ የተገኘ እውቀት፣ ገጠመኝ።

***ሞከሸ**

ተሞካሸ ግ 1. ተቆላመጠ፥ በቁልምጫ ተጠራ። 2. ተሞገሰ።

አሞካሸ ግ 1. አቆላመጠ፥ በቁልምጫ ጠራ። 2- አሞገሰ።

ሞከተ ግ 1. ተባእት በግን ወይም ፍየልን አኮላሽቶ ወይም ቀጥቅጦ ቀለበ፥ አወፈረ፥ አደለበ፥ አሰባ። 2. ደለበ፥ ወፈረ፥ ሰባ።

ሙክት ስ ተኮላሽቶ ወይም ተቀጥቅጦ የተቀለበና ያሰባ ወፍራም በግ ወይም ፍየል።

ሞከከ ግ 1.በጣም በሰለ (እንደኮሽም፥ ቀጋ፥... ያሉ ፍራፍሬ)። 2.(ዘይ.) በጣም ሰከረ።

ሙክክ አለ ዝ.ከ.

ሞክሼ ቅ 1. አንድ አይነት መጠሪያ ስም ያላቸው(ሰዎች)። *ሞክሼ ናቸው*። 2. ተመሳሳይ መጠሪያ ወይም ድምፅ ያላቸው (ሆሄያት ወይም ፊደላት)። *"አ"ና "ዐ" ሞክሼ ሆሄያት ናቸው*።

ሞክድ "ሙግድ"ን ተመ.

ሞዘቀ ግ በሙዚቃ መሳሪያ ተጫወተ፥ አዜመ።

ሙዚቃ ስ ለጆሮ ተሰሚነት ያለው፥ ስሜትን ሊቀሰቅስ የሚችል፥ በመሳሪያና በሰው ድምፅ ወይም በመሳሪያ ብቻ የተቀናበረ ጣእመ ዜማ።

የሙዚቃ መሳሪያ ስ ልዩ ልዩ አይነት ጣእመ ዜማዎችን ለማውጣት፥ ለመጫወት የሚያስችል እንደክራር፥ ዋሽንት፥ ጊታር፥ ፒያኖ፥... ያለ መሳሪያ(ስእሉን በሚቀጥለው ገፅ ተመ.)።

የሙዚቃ ቤት ስ በቴፕ ክር፥ በሸክላ፥... የተቀረፁ ልዩ ልዩ ዘፈኖችና የሙዚቃ ቅንብሮች የሚሸጡበት መደብር።

ሙዚቀኛ ቅ በኦርኬስትራ፥ በባንድ፥... ውስጥ ተቀጥሮ የሙዚቃ መሳሪያዎችን የሚጫወት።

ሞዘዘ ግ ቸከ፥ ለዛ አጣ፥ አሰለቸ።

ሙዝዝ ቅ ሞዛዛ።

ሞዛዛ ቅ ለዛ ቢስ፥ ቸካ።

ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች



1. ክራር
2. መለከት
3. ዋሽንት
4. እምቢልታ
5. ከበሮ
6. ነጋሪት
7. አታሞ
8. ማሲንቆ
9. ፋንፋን
10. ቃጭል
11. በገና
12. ፀናፅል

ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች



1. አኮርዲዮን
2. ክላርኔት
3. ቫዮሊን
4. ቪዮላ
5. ሃርሞኒካ
6. ትራምፔት
7. ፒያኖ
8. ጊታር
9. ሳክሰፎን

ተሟዘዘ ግ ተመናቸከ፣ ለዛ ኣጣ።

ሞዠቀ ግ ፈገፈገ፣ ፈተገ (ብዙ ጊዜ ሻካራ በሆነ ነገር)።

ሞያ "ሙያ"ን ተመ.

ሞያሌ "ሙጃሌ" ን ተመ.

ሞይደር ስ ወተት መስል ፈሳሽ የሚወጣው ሃረግ የሚመስል የእፅዋት ኣይነት።

***ሞደሞደ**

ሞድሟዳ ቅ ኣባባቂ፣ ወሬኛ።

ተሞዳሞደ ግ ኣሳበቀ፣ ወሬ ከወዲያ ወዲህ ኣመላለሰ።

ኣሞዳሞደ ዝ.ከ.

ሞዴል^{1} ስ 1. ካሁን በፊት ላለ ወይም ወደፊት ለሚሰራ ነገር እንደምሳሌ፣ እንደማስረጃ ሆኖ የሚቀርብና የሚታይ ናሙና፣ ቅርፅ፣ ምስል። 2. ለስእልና ቅርፃቅርፅ ሙያ ጥናት ሲባል በሙያተኞች ፊት በተለያየ ኣቋም በመሆን ልዩ ልዩ ኣካላዊ ቅርፆችን፣ ስሜቶችን፣... የሚያሳይ ወይም የምታሳይ (ሰው)። 3. በተለያየ ፋሽን የተሰፉ ልብሶችን፣ ጫማዎችን፣ ጌጣጌጦችን፣... በመልበስ ለንግድ የሚያስተዋውቅ፣ የሚያሳይ ጥሩ የሰውነት ቅርፅና ቁመና ያለው ሰው (ብዙ ጊዜ ሴት)።

ሞዴል^{2} ስ 1. የተለያዩ ጉዳዮችን ለመመዝገብ የተዘጋጀ ቅፅ ወይም ሰነድ ወይም ካርኒ። 2. መስሪያ ቤቶች ለሰራተኞቻቸው በቅድሚያ የሚሰጡትና ከደመወዛቸው ላይ ተቆራጭ ሆኖ የሚከፈል የገንዘብ ብድር።

ሞዴስ ስ ሴቶች በወር ኣበባ ጊዜ ከሙታንታ ውስጥ እድርገው የሚታጠቁት ከጥጥና ከለሰለሰ ጨርቅ የሚሰራ የወር ኣበባ ማምጠጫ።

ሞድ ስ ፋሽን። *በአዲሱ ሞድ የተሰፋ ቀሚስ።*

ሞድሟዳ "*ሞደሞደ" ስር ተመ.

ሞጀረ ግ 1. ሳይመጥን፣ ሳይለካ በብዛት ጨመረ። *ከወጡ ውስጥ ጨውን ሞጀረችው።* 2 የማይገባውን ወይም የማይስማማውን ነገር ጨመረ። *ላፈፉን ላይት ውስጥ ሞጀረበት።*

ሞጀጀ ግ 1. ሞገገ፣ ከሳ፣ መነመነ፣ ሰሰበለ፣ ቀጠነ። 2. ረዘመ፣ ተንቀዋለለ።

ሞጃጃ ቅ 1. ሞጋጋ፣ ከሲታ፣ መንማና። 2. ረዥም፣ ቀውላላ።

ሞጃ ስ ሃብታም፣ ዲታ፣ ባለጠጋ።

***ሞገሰ**

ሞገስ ስ ክብር፣ ተወዳጅነት።

ሞገስ ኣገኘ ተከበረ፣ ተወደደ።

ሙገሳ ስ ምስጋና፣ አድናቆት፣ ውዳሴ።

ተሞገሰ ግ ተመሰገነ፣ ተወደሰ።

ኣሞገሰ ግ ኣመሰገነ፣ ኣወደሰ።

ሞገተ ግ 1. በንብረት፣ በወንጀል፣... ምክንያት ፍርድ ቤት ወይም ሸንጎ ላይ ተከራከረ። 2. ነዘነዘ፣ ጨቀጨቀ፣ ተከራከረ።

ሙግት ስ በፍርድ ቤት ወይም በሸንጎ ላይ ከሳሽና ተከሳሽ የሚያደርጉት ክርክር፣ የሚነጋገሩበት ጉዳይ፣ እሰጥ ኣገባ።

ተሟገተ ግ 1. ኣንድ ኣቋም ይዞ "እንዲህ ነው" ወይም "እንዲህ ይሁን" እያለ ተከራከረ። 2. ተጨቃጨቀ።

ኣሟገተ ግ 1. ኣከራከረ፣ ኣጨቃጨቀ(ጉዳዩ)። 2. በዳኝነት ተሰይሞ ከሳሽና ተከሳሽን ኣነጋገረ፣ ኣከራከረ።

ሞገደ ግ ኣወከ፣ እምቢተኛ ሆነ፣ ኣስቸገረ፣ ኣሻፈረኝ ኣለ።

ሞገድ ስ እልህ፣ ሃይል።

ሞገደኛ ቅ ሃይለኛ፣ እልሀኛ፣ እኔ ያልኩት ብቻ ይሁን ባይ።

ሞገድ ስ 1. በነፋስ ምክንያት የሚፈጠር የባህር መናወጥ። 2. በአየር ላይ የሚተላለፍ የድምፅ ስርጭት።

ሞገገ ግ በጣም ከሳ፣ ኣጥንቱ ገጠጠ።

ሞጋጋ ቅ ከሲታ፣ ኣጥንቱ የገጠጠ።

ሞጌ ዝ.ከ.

ሞጌው ወጣ እጅግ ከሳ፣ መነመነ፣ ኣጥንቱ ገጠጠ።

ሞጋሳ

የሞጋሳ ልጅ (ሞጋሳ) ስ የማደጎ ልጅ።

ሞጋጋ "ሞገገ" ስር ተመ.

ሞጌ ዝ.ከ.

ሞግዚት ስ 1. ልጅን የሚያሳድግ፣ የሚንከባከብ ቅጥር ሰራተኛ። 2. ልጅ ራሱን እስከሚችል ድረስ በበላይነት የሚያስተዳድር፣ የሚንከባከብና ስለሱ ሆኖ ማንኛውንም ጉዳይ የሚፈፅም ሰው።

ሞግድ "ሙግድ"ን ተመ.

ሞጠለቀ ግ ሰረቀ፣ መነተፈ፣ ሞጨለፈ።

ሙጥልቅ ቅ ዋና ሌባ።

ሞጠለቅ (ሞጥላቃ) ዝ.ከ.

ሞጠሞጠ ግ ሾለ።

ሙጢ [ኣፍ] ቅ ነገረኛ፣ ምላሰኛ።

ሞጥሟጣ ዝ.ከ.

ተሞጣሞጠ ግ ተሳደበ፣ ብዙ ተናገረ፣ ለፈለፈ።

ኣሞጠሞጠ ግ 1. ሾለ፣ ኣሞለሞለ። *ቁስሉ ኣምጥሙጧል።* 2. ለመሳደብ ወይም ለመናገር ተዘጋጀ፣ ኣፉን ኣሾለ።

ሞጣህት ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) በኣንገት እንዲጠለቅና በደረት በኩል ወደታች እንዲንጠለጠል ሆኖ የተሰራ፥ ቄስ በቤተክርስቲያን ውስጥ ሲያገለግል ከሚለብሳቸው ኣልባሳት ኣንዱ።

ሞጣህት

ሞጥሟጣ "ሞጠሞጠ" ስር ተመ.

ሞጨለሰ "መጨለሰ"ን ተመ.

ሞጨለፈ ግ 1. ቀማ፥ ነጠቀ (በድንገት)። 2.ሰረቀ።

ሞጭለፍ(ሞጭላፊ) ቅ ቀማኛ፥ ነጣቂ፥ ሌባ።

ሞጨሞጨ ግ ኣይናር ያዘ፥ እንባ ኣቀረረ፥ ተጨናበሰ (ኣይን)።

ሞጭሟጫ ቅ ኣይኑ ኣይናር የያዘ፥ እንባ ያቀረረ፥ ጨንባሳ።

ኣሞጨሞጨ ግ ሞጨሞጨ።

ሞጠጠ (ሟጠጠ) ግ 1. ኣጣበቀ። 2. ተጣበቀ፥ ያዘ።

ሙጭጭ ኣለ ግ 1. ኣልለይ፥ ኣልለቅ ኣለ፥ ተጣበቀ። *ሰውየው ልጅቷ ላይ ሙጭጭ ኣለ።* 2. ድርቅ፥ ሙዝዝ ኣለ። *በሰው ቤት ሙጭጭ ኣለ።*

ሙጫ ስ 1. ከዛፍ የሚወጣና ፈሳሽነት ያለው መጣበቅ። 2. ከያዘ የማይለቅ።

ሞጫጨረ "ሟጨረ" ስር ተመ.

ሞጭሟጫ "ሞጨሞጨ" ስር ተመ.

ሞፈር ስ ወፈር ረዘም ካለ እንጨት ተጠርቦ የሚሰራና ከቀንበር ጋራ በምራን የሚያያዝ የእርሻ መሳሪያ።

ሞፈር ሰቀል ቅ (የን.ኣነ.) በቅርብ ጊዜ የእርሻ ስራውን ትቶ ከተማ የገባ ገበሬ፥ ባላገር።

ሞፈር ዘመት [እርሻ] ስ ካሉበት ኣካባቢ ርቆ በመሄድ የሚታረስ እርሻ (ኣስያየሙ ሞፈር ተሸክሞ መሄድን ያመለክታል)።

ሞፎ ስ 1. የጥራት ደረጃው ዝቅተኛ የሆነ ቶርኖ፥ ዳቦ። 2.(ዘይ.)በጣም ወፍራም ሆኖ ኣቅም የሌለው (ሰው)።

ሟ የ "መ" ፊደል ፍንልቅ ዘር።

ሟለጠ ግ 1. በጣም ለዘ፥ ለሰለሰ፥ ሸካራነት የሌለውና ዳላጣ ሆነ (ለምሳሌ ያልተወተረ የእጅ ወፍሮ)። 2. ስራ ፈትቶ፥ ማጋጣ ሆነ።

ሟላጣ ቅ 1. ሸካራ ያልሆነ፥ በጣም የለዘበ፥ የለሰለሰ፥ ዳላጣ። 2. (ዘይ.) ስራ ፈት፥ ዋልጌ።

ኣሟለጠ ግ 1. ኣዳለጠ። 2. ኣማገጠ፥ ዋልጌ ኣደረገ።

ሟለጨ ግ ድጥ ሆነ፥ ዳለጠ፥ ኣልያዝ ኣልጨበጥ ኣለ።

ሙልጭልጭ ቅ 1. ዳላጣ፥ ለመያዝ ወይም ለመጨበጥ፥ ለመርገጥ የሚያስቸግር። 2. (ዘይ.) በቃሉ የማይገኝ፥ ኣታላይ። 3. ሲያገኙት ሲፈልጉ የማይገኝ፥ እዚህ ነው ሲሉት ሌላ ቦታ የሚገኝ (ሰው)።

ሙልጭልጭ ኣለ ግ 1. ኣልያዝ ኣልጨበጥ ኣለ፥ ማላጋ ሆነ። 2. (ዘይ.) በቃሉ የማይገኝ ሆነ፥ ዋሸ፥ በፈለጉት ቦታ ሳይገኝ ቀረ፥ ኣልገኝ ኣለ።

ተሙለጨለጨ ገ.ከ.

ኣሙለጨለጨ ግ ኣልያዝ ኣልጨበጥ ኣለ፥ ማላጋ ወይም ዳላጣ ሆነ።

ኣሟለጨ ግ ኣልያዝ ኣልጨበጥ ኣለ፥ ኣልረገጥ ኣለ፥ ማላጋ ሆነ፥ ኣዳለጠ።

ሟሟ ግ ጠጣር የነበረው ነገር ቀለጠ፥ ወደ ፈሳሽነት ተለወጠ፥ ሟሸሸ።

ሟረ

ኣሟረ ግ ቀለሰ።



*ሟረተ

ሟርት ስ 1. የመጥፎ ነገር ትንቢት፥ ምልኪ (ለምሳሌ ውሻ ካነጠሰ፥ እንቅፋት ከመታ፥..., መጥፎ ነገር ሊያጋጥም ይችላል የሚል እምነት)። 2. በሌላው ላይ መጥፎ ነገር ወይም ጉዳት እንዲያደርስ ተብሎ ጉዳቱ እንዲደርስበት በተፈለገው ሰው ወይም አካል አካባቢ የሚቀበር፥ የሚቀመጥ ወይም የሚጣል፥... መተት፥ ደንቃራ።

ሟርተኛ ቅ 1. በሌላው ላይ ክፉ የሚተነብይ፥ የሚመኝ፥ የሚያሟርት። 2. ሟርት ወይም ደንቃራ የሚጥል።

አሟረተ ግ 1. በሌላው ላይ መጥፎ፥ ክፉ ነገር ተነበየ። 2. ደንቃራ ጣለ፥ መተት አደረገ።

ሟሰሰ ግ ነጨ፥ ነቀለ (ሳርን፥ እህልን፥...በእጅ)።

*ሟሸ

ሙሽት ስ አዲስ በተሟሸ ምጣድ ላይ ወዲያው የሚጋገር እንደቂጣ ያለ እንጀራ።

አሟሸ ግ 1. እንደ ምጣድ፥ ድስት፥... ያለን አዲስ የሸክላ እቃ እንዲጠነክር፥ እንዲለዝብና ለተፈለገው አገልግሎት ብቁ ሆኖ እንዲገኝ በእሳት ለበለበ፥ እንደ ጥፍጥሬ፥ ጎመን ዘር፥... ባለ የቅባት እህል አሸ፥ ወለወለ። 2. (ዘይ.) ለመጀመሪያ ጊዜ ሰራ፥ አከናወነ ወይም በአንድ ነገር ለመጀመሪያ ጊዜ ተጠቀመ።

ሟሸሸ ግ በመተንፈስ፥ በመከሳት፥ በመድረቅ፥... ቀድሞ ከነበረው መጠን ቀነሰ፥ ጎደለ፥ አነሰ፥ ከሰመ።

ሟች “ሞተ” ስር ተመ.

ሟነነ ግ እየቀጠነ፥ እያነሰ ሄደ (ብዙ ጊዜ ለፈትል)።

ሞናና (ሙናና) ቅ አነስ፥ ቀጠን ያለና የሚያምር።

አሟነነ ግ አቀጠነ፥ ቀጭን አደረገ (ፈትልን)።

ሟገ (ሟጀ) ግ 1. ቀለም፥ ቅባት፥... ቀባ፥ ለቀለቀ። 2. አለዘበ፥ አለሰለሰ፥ ፈገፈገ (ጅማትን፥ ቡትርን፥...)።

ሟደደ ግ 1. ከስሩ ጥርግ አድርጎ፥ ቆረጠ። 2.(ዘይ.) ሰረቀ፥ ሞለጨ።

ሟደድ ቅ ጭርስ አድርጎ ጠራርጎ የሚወስድ ሌባ።

ሟጀ “ሟገ”ን ተመ.

ሟጠጠ ግ 1. ምንም ሳያስቀር ጥርግ አድርጎ አነሳ፥ ወሰደ፥ ባዶ አደረገ፥ ጨረሰ (ቅቤን፥ ድልህን፥ ቡኮን፥...)። 2. ሰረቀ፥ ባዶ አስቀረ።

ሙጣጭ ቅ የመጨረሻ፥ ተሟጦ የቀረ፥ እሳቂ።

ሟጣጭ [ሌባ] ቅ ምንም ሳያስቀር ጠርጎ የሚወስድ፥ ሞሽላቃ ሌባ፤ ሟደድ፥ ሌባ።

ተሟጠጠ ግ አለቀ፥ ባዶ ቀረ።

አሟጠጠ ግ ጨረሰ፥ ባዶ አስቀረ።

ማሟጠጫ ቅ የመጨረሻ። እንጌ. ለወቃጆቹ ማጓጠጫ [ሌጅ] ነው።

ሟጨ ግ ፋቀ፥ ጠረገ፥ ፈገፈገ፥ አፀዳ (ጥርስን)።

መሟጫ (ማሟጫ) ስ የጥርስ መፋቂያ።

አሟጨ ግ ሟጨ።

ሟጨረ ግ 1. በጥፍሩ ወይም በሹል ነገር ጫረ፥ አቆሰለ፥ ቧጨረ። 2. ላይ ላዩን አረሰ።

ሙጭርጭር ቅ የተበላሸ፥ የማይነበብ (ፅሁፍ)።

ሞጫጨረ ግ 1. ቧጨረ፥ ሰለጠጠ፥ ሰነጣጠቀ። 2. የተበላሸ፥ የማይነበብ ፅሁፍ ፃፈ። 3. እንደነገሩ ፃፈ፥ በሚገባ ያልታሰበበትና ያልተለፋበት ፅሁፍ አዘጋጀ።

ሟጨራ^1 ስ ከጤፍ ጋር የሚበቅል ፍሬው ጤፍ የሚመስል ሳር።

ሟጨራ^2 **(ሟጫራ)** በእንጀራ ሰበከት ላይ የሚገኝ፥ እጅ ላይ የሚጣበቅና አራራ የሚመስል ነገር።

ሟጨጨ “ሞጨጨ” ስር ተመ.

ረ

ረ በዚህ መዝገበ ቃላት ፊደል ተራ መሰረት ከ "ሠ" ፊደል ዘር ቀጥሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል (ግእዙ ሆሄ)፡፡

ረሀጥ ቅ ሙያ የሌላት ሰነፍ፥ ገልቱ(ሴት)፡፡

ረሃብ "ራበ" ስር ተመ.

ረሃብተኛ ዝ.ክ.

ረመረመ ግ በእግር ረገጠ፤ ረጋገጠ፥ ጠቀጠቀ፡፡

ተረመረመ ግ በእግር ተረገጠ፥ ተረጋገጠ፡፡

***ረመሰመሰ**

ርምስም አለ ግ ተርመሰመሰ፡፡

ተርመሰመሰ ግ በብዛት ሆኖ ተንቀሳቀሰ፥ ተሳወሰ፡፡

አርመሰመሰ ግ 1. በብዛት አንቀሳቀሰ፡፡ 2. አተራመሰ፡፡

***ረመደ**

ርምድ ስ በሩካቤ ስጋ ምክንያት ወደ ሌላው የሚተላለፍ የቂጥኝ ቁስል በሽታ አይነት፡፡

[እ]ርምጃ ስ 1. አካሄድ፤ አረማመድ፡፡ 2. በመራመድ ሂደት ላይ ባሉት ሁለት እግሮች መካከል ያለ የቦታ ርዝመት፥ መጠን፡፡ 3. እድገት፥ መሻሻል፡፡ *ስራው ርምጃ አሳይቷል፡፡* 4. አንድ ግብ ለመድረስ፥ አላማን ለማሟላት የሚደረግ ተግባራዊ እንቅስቃሴ፤ ውሳኔ፡፡ *አንድ ርምጃ ካልተወሰደ ነገሩ ፍፃሜ አያገኝም፡፡* 5. ቅጣት፡፡ በጥፋተኞቹ ላይ ርምጃ ተወሰደ፡፡

ራመድ አለ ግ ሄድ አለ፤ ተራመደ፡፡

ራመድ ራመድ አለ ግ እየፈጠነ ሄደ፥ ተራመደ፡፡

ተራመደ ግ 1. ሄደ፤ ገሰገሰ፡፡ 2. አልፎ፤ ዘሎ፥ ተሻግሮ ሄደ፡፡ 3. እድገት ወይም መሻሻል አሳየ፡፡

ተራማጅ ቅ 1. ሂያጅ፤ ፈጣን፥ ገስጋሽ፡፡ 2. የህብረተሰብን እድገት ወደፊት ለማራመድ የሚረዳ (አስተሳሰብ፤ አዋጅ፥ አመለካከት፥...)፡፡ ስ 3. በአንድ የታሪክ ወቅት የህብረተሰብን እድገት ወደፊት ለማራመድ የሚጥር፤ የሚታገል ሰው፡፡

መራመጃ "**መረማመጃ**"ን ተመ.

ተረማመደ ግ 1. ተላለፈ፤ ተሸጋገረ፡፡ 2. ረግጦ አለፈ፥ ተሻግሮ ሄደ፡፡ 3. አደገ፤ ወደፊት ሄደ (በማእረግ፥ በትምህርት)፡፡

መረማመጃ(መራመጃ) ስ መተላለፊያ፥ መሸጋገሪያ፥ መወጣጫ፡፡ *መረማመጃ የለም መፈናፈኛ የለም፥* ጠባብ ነው፡፡

አራመደ ግ 1. አስኬደ፡፡ *እግሩ አላራምድ አለው/መንገዱ ድንጋያማ በመሆኑ እንደልብ አያራምድም፡፡* 2. አካሄደ፤ አስፋፋ፥ አቀነቀነ (ርእዮተ አለም)፡፡ *አገሪቱ የሶሻሊስትን ርእዮተ አለም ታራምዳለች፡፡*

አራምዶ አየ አሻግሮ አየ፤ ተመለከተ፡፡

አራማጅ ቅ አቀንቃኝ፡፡ *የሶሻሊዝም ፍልስፍና አራማጅ፡፡*

አረማመደ ግ 1. አሸጋገረ፥ አስተላለፈ፡፡ 2. አራቀ፤ አሸሸ፡፡ *ሌባው ከብቶቹን አረማመዳቸው፡፡*

አረማመድ ስ የእግር አጣጣል፤ አካሄድ፡፡

ረመዳን ስ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች፥ ፀሃይ ወጥታ እስከምትጠልቅ የሚፆሙበት በእስልምና የቀን አቆጣጠር ዘጠነኛው ወር፡፡

ረመጠ ግ ረመጥ ውስጥ ከተተ፥ ጠመረ፡፡

ረመጥ ስ የደቀቀ ፍም፤ ፍምነት ያለው አመድ፡፡

ረሞጫ ስ ከፀሃይ ግለት የተነሳ እንደረመጥ የሚፋጅ አሸዋ፤ አካባቢ፡፡

ርሚጦ (ርሚጦሽ) ስ ሊጡን በቅጠል ሸፍነው ረመጥ ውስጥ በማስገባት የሚያበስሉት ሙልሙል ዳቦ (ብዙውን ጊዜ ለውሻ የሚዘጋጅ)፡፡

[እ]ርምጥምጥ ([እ] ርሙጥሙጥ) ቅ ልኩስኩስ፥ ፅዳት የለሽ፡፡

ተርመጠመጠ (ተርሞጠሞጠ) ግ በቆሻሻ፥ በማይረባ ቦታ ተልኮሰኮሰ፡፡

አረማጥ ቅ 1. አመዳም፥ ጥላሸታም፥ ፅዳት የሌለው፡፡ 2. ጥቁርቁር ያለ፤ ጠቋራ፡፡

አርመጠመጠ (አርሞጠሞጠ) ግ አልኮሰኮሰ፥ አጎደፈ፥ በቆሻሻ ነገር በከለ፥ ለዋወሰ፡፡

ረሰረሰ ግ ረጠበ፤ ራሰ፤ ወረዛ፥ ረዘረዘ፡፡

አረሰረሰ ግ አራሰ፥ አረጠበ፥ አወረዛ፡፡

ረሰሰ ግ በእርሳስ ምልክት አደረገ፡፡

[እ]ርሳስ ስ 1. ከብደትና ለስላሳነት ያለው፥ በቀላሉ የሚቀልጥ የማእድን አይነት፡፡ 2. የጥይት አረር፡፡ 3. ለመፃፊያ፤ ለመሳያ የሚያገለግል ከእርሳስ ማእድን የሚሰራ የፅህፈት መሳሪያ፡፡ (ስእሉን ፅህፈት መሳሪያ ስር ተመ.)

ረሳ ግ 1. ዘነጋ፤ ሳተ፥ ማስታወስ አቃተው፡፡ 2.በመዘንጋት፥ ባለማስታወስ አንድን ነገር ሳይሰራ፥ ሳያከናውን፤... ቀረ፡፡ 3. ተወ፥ ከሃሳብ አወጣ፤ ትኩረት ሳይሰጥ ቀረ፡፡ *ምጡን እርሸው ልጁን አንሸው /ሃብት ሲያገኝ የቀድሞ ጓደኞቹን ረሳ፡፡*

አትርሳ አንድ ሰው ብድሬን እመልሳለሁ

ለማለትና ቂም መያዙን ለማሳወቅ የሚጠቀምበት አነጋገር:: *መፅሃፉን አውሰኝ ብልህ ከለከልከኝ አይደል? አትርሳ!*

እርስት አደረገ ግ 1. ዘነጋ:: 2. ባለማስታወስ፥ በመዘንጋት ሳይሰራ፥ ሳያከናውን ቀረ::

ተረሳ ግ 1. ሳይታወስ ቀረ፣ ተዘነጋ፣ ከአእምሮ ጠፋ:: 2. ባለመታወሱ፥ በመዘንጋቱ ተተወ ወይም ቀረ:: *ቦርሳዬ እቤት ተረሳ::*

ተረሳሳ ግ እየተተወ፣ እየቀረ፣ እየተዘነጋ ሄደ::

አረሳሳ ግ 1. አዘናጋ:: 2. ሃዘንን፥ ንዴትን አስተወ፤ አፅናና::

ማረሳሻ ስ ማባበያ፥ ማፅናኛ፥ማስረሻ፣ እንዲረሳ ማድረጊያ::

ረሸነ ግ ሰውን በፍርድም ይሁን ያለፍርድ በጥይት ደብድቦ ገደለ::

ተረሸነ ግ በጥይት ተደብድቦ ሞተ::

ረሽ ስ ለአደን የሚያገለግልና ጥይቱ ብዙ ፍንጣሪ ያለው ጠበንጃ::

ረቀረቀ¹ ግ 1. መሳልስ መታ፥ ደበደበ:: 2.ረዘም ላለ ጊዜ ጣለ፣ ዘነበ:: *ዝናቡ ሲረቀርቀው አደረ::*

ረቀረቀ² ግ ሻጠ፣ ሰካ፣ ሰነቀረ፣ ወጋ::

***ረቀረቀ**

ተስረቀረቀ ግ 1. ተንሰቀሰቀ አለቀሰ:: 2. ስሜት በሚነካ መልክ ተንቆረቆረ (የድምፁ፥ የዜማው ቃና)::

አስረቀረቀ ግ 1. አንሰቀሰቀ፥ አስለቀሰ:: 2. ስሜትን በሚነካ መልክ (ዜማን) አንቆረቆረ::

ረቀቀ ግ 1. አነሰ፥ ጥቃቅን ወይም ደቃቃ ሆነ:: 2. ደቀቀ፥ ላመ፥ ተፈጨ (የመገበሪያ ስንዴ):: 3. ቀጠነ፥ መነመነ:: 4. ለመረዳት፣ ለማወቅ የሚያስቸግር፥ ጥልቅ ወይም ውስብስብ ሆነ:: 5. የመጀመሪያና ያላለቀለት፥ በግርድፍ ያለ (የንግግር፥ የፅሁፍ፥... ረቂቅ) ፅሁፍ ተዘጋጀ::

በረቀቀ ዘዴ በብልሃት፥ በማይታወቅ ሁኔታ:: *ሌባው በረቀቀ ዘዴ እቃ ከሳጥን ውስጥ አውጥቶ ወሰደ::*

ረቂቅ ቅ 1. ግዝፈት ወይም ትልቅነት የሌለው፥ መጠኑወይም ውፍረቱ በጣም ትንሽና ደቃቃ የሆነ:: 2.ትልቅነት ስለሌለው ወይም ደቃቃ በመሆኑ አስቸጋሪ የሆነና ከፍተኛ ጥበብ የሚጠይቅ (የጌጣጌጥ፥የእደጥበብ፥...ስራ)::3.በአይን የማይታይ፥ በእጅ የማይዳሰስ::4.ደቃቅ በሆነ (ጉልህ ባልሆነ) በትንንሽ ፊደል የተፃፈ (ፅሁፍ):: 5. ውስብስብና ጥልቅ የሆነ፣በቀላሉ መረዳት የማይቻል (አስተሳሰብ፣ የሳይንስ እወቀት፥ ዘዴ፥...):: ስ 6.የተፈጨ፥ የደቀቀ፥ የሳመ የመገበሪያ ስንዴ ዱቄት:: 7. ስለ አንድ ነገር በመጀመሪያ በወረቀት ላይ የሰፈረ ሃሳብ (እንዳስፈላጊነቱ ሊታረም የሚችል):: 8. ለውሳኔ፥ ለውይይት የቀረበ ፅሁፍ::

ረቂቅ አዘጋጀ/ፃፈ እንዳስፈላጊነቱ ሊታረም የሚችልና ለመንደርደሪያ የሚሆን የመጀመሪያ ፅሁፍ ፃፈ፥ አቀረበ::

ረቂቅ ነፍሳት ስ በአካል ያሉና ያለ ማጉሊያ መነፅር መታየት የማይችሉ ነፍሳት::

ረቂቅ አዋጅ ስ ህግ ሆኖ እንዲወጣ፣ እንዲወሰን፣ እንዲፀድቅ ለፓርላማ፥ ለምክር ቤት፥ ለሸንጎ የቀረበ አዋጅ::

ርቅት ስ ጥልቀት፣ ረቂቅነት::

ተረቀቀ ግ የመጀመሪያ ደረጃ (ፅሁፍ፥ አዋጅ፥...) በወረቀት ሰፈረ::

ተራቀቀ ግ በሳይንስ፥ በፍልስፍና፥... መጠቀ፥ ተፈላሰፈ፥ ተጠበበ፥ ተመራመረ:: *በሳይንስ ተራቀቀ::*

አረቀቀ ግ 1. ፈጨ፥ አደቀቀ፥ አላመ:: 2. በትናንሽ የፊደል ቅርፅ ፃፈ:: 3. ቃል አውጣጣ፣ ለመጀመሪያ ወይም ለመንደርደሪያ የሚሆን ሃሳብ በፅሁፍ አዘጋጀ::

አርቃቂ ቅ ፍሬ ሃሳቦችን አጠናቅሮ የመጀመሪያ ወይም መነሻ የሚሆን ፅሁፍ የሚያዘጋጅ:: *አርቃቂ ኮሚቴ::*

አራቀቀ ግ 1. በእውቀት የጠለቀ፥ የረቀቀ እንዲሆን አደረገ:: *የከፍተኛ ትም/ቤቶች መብዛት ሃገሪቱን በሳይንስ ጥበብ ሊያራቅቃት ቻለ::* 2. ስራውን፥ ጥበቡን የበለጠ ጥልቅ፥ ውብ፥ ጥርት ያለ እንዲሆን አደረገ:: 3. አመሰጠረ (ቅኔን)::

ረበረበ ግ 1. ደረደረ፥ ደራረበ፥ አነባበረ (እንጨትን፥ ብረትን፥...):: 2. ረፈረፈ፣ አነባበረ፥ አንዱን በሌላው ላይ ጣለ:: *ጠላቶቹን በጥይት ረበረባቸው::* 3. አርከፈከፈ፣ ረጨ:: 4. መንገድን (ድንጋይ በማንጠፍ፥...) አስተካከለ::

መረባረብ የ"ርብራብ"ን 1ኛ ፍቺ ተመ.

ርብራብ ስ 1. ድልድይን ወይም ንጣፍን ለመስራትና ለመደልደል የሚያገለግል እንጨት፥ ብረት፥ ድንጋይ፥...፤መረባርብ:: 2. እንጨት ወይም ብረት በመደርደር የተሰራ::

ርብራብ አልጋ ስ በአግድም የተደረደረ የእንጨት ንጣፍ ወይም ርብራብ ያለው አልጋ::

ርብርብ ስ አንድን ነገር ፍፃሜ ላይ ለማድረስ የሚደረግ የጋራ ጥረት፣ የጋራ እርምጃ፣ ትግል::

ተረበረበ ግ 1. ተደለደለ፥ ተስተካከለ:: 2. በውሃ ተርከፈከፈ፣ ተረጨ::

ተረባረበ ግ 1. ተጋገዘ፥ ተረዳዳ፥ ሃይሉን አስተባበረ:: 2. ተሻማ:: *ልብሱን ለመግዛት ሰው ሁሉ ተረባረበ::*

አረበረበ ግ 1. ውሃን ረጨ፥ አርከፈከፈ። 2. ንግግር አበዛ፥ ለፈለፈ። 3. (ዘይ.) ሽርጉድ አበዛ፥ አዘባዘበ።

አረብራቢ ቅ ለፍላፊ፥ አለሁ አለሁ ባይ።

ረበሸ ግ 1. በጠበጠ፥ አወከ፥ አስቸገረ፥ ጠብ አነሳ። 2. ሰላም ነሳ፥ እረፍት ነሳ።

ረባሽ ቅ በጥባጭ፥ አዋኪ።

ረብሻ ስ ሁከት፥ ጠብ፥ ትርምስ፥ ብጥብጥ፥ ግርግር።

ረብሸኛ ቅ 1. በጥባጭ፥ አዋኪ። 2. ተደባዳቢ፥ ጠብ ወዳድ።

ተረበሸ ግ 1. ተበጠበጠ፥ ግርግር ተፈጠረ። 2. ተጨነቀ፥ ተጠበበ፥ መንፈሱ ታወከ።

ተረባበሸ ግ ተተራመሰ፥ ምስቅልቅሉ ወጣ።

ተራበሸ ግ ተበጣበጠ፥ ተጣላ።

አራበሸ ግ አጣላ፥ አጋጨ።

ረበበ ግ 1. ሰፈፈ፥ ተንዣበበ፥ አንዣበበ (በአየር ላይ)። 2. አጠላ፥ ጋረደ፥ ድባብን ዘረጋ። 3. አደረ፥ መጣ፥ ሰፈነ። *መንፈስ ቅዱስ ረበበት።*

***ረበተበተ**

[እ]ርብትብት ቅ 1. ፈሪ፥ ድንጉጥ። 2. ሽቁጥቁጥ። *እገሌ ለጓደኞቹ እርብትብት ነው።*

[እ]ርብትብት አለ ግ ተርበተበተ።

ተርበተበተ ግ ፈራ፥ ደነገጠ፥ ተንቀጠቀጠ፥ ራደ።

አርበተበተ ግ አንቀጠቀጠ፥ አርበደበደ።

***ረበየ**

ተረባየ ግ 1. ተረገጠ፥ ተረመረመ። 2. ተበራየ፥ ተወቃ፥ ተሄደ (የእህል ነዶ)።

አረባየ ግ 1. ረገጠ፥ ረመረመ፥ ጠቀጠቀ። 2. አበራየ፥ ወቃ፥ አሄደ።

***ረበደበደ**

[እ]ርብድብድ ቅ ፈሪ፥ ድንጉጥ፥ እርብትብት።

[እ]ርብድብድ አለ ግ ተርበደበደ።

ተርበደበደ ግ ተንቀጠቀጠ፥ ራደ፥ ፈራ፥ ተርበተበተ።

አርበደበደ ግ አስፈራ፥ አስጨነቀ፥ አንቀጠቀጠ፥ አርበተበተ።

ረቡእ (ሮብ) ስ በማክሰኞና በሃሙስ መካከል ያለው ቀን ስም፤ ከእሁድ ጀምሮ ሲቆጠር የሳምንቱ አራተኛ ቀን።

ረባ ግ 1. በመውለድ፥ በመዋለድ በዛ፥ በረከተ፥ ተጨመረ። 2. ጠቀመ፥ ፈየደ። *ላሀያ ለዛ ምን ረባ።* 3. (ሰዋ.) ግሱ ወይም አንድ ግሳዊ ቃል በጊዜ፥ በቦታ፥ በመደብ ተተነተነ፥ ተዘረዘረ።

አይረባም ጥራት፥ ጥንካሬ፥ ረዥም አገልግሎት የለውም። *የገዛው ሰዓት አይረባም።*

ረብ ስ ጥቅም፥ ፋይዳ።

ርቢ ስ 1. እርባታ፥ ማራባት፥ ማዋለድ፥ ማብዛት። *ከብት ርቢ።* 2. የቤት እንስሳትን ከሌላ ሰው በውሊታ ወስዶ በመቀለብና በማዋለድ የሚገኙትን ውልዶች ከእንስሳቱ ባለቤት ጋር እኩል የመካፈል ልምድና ተግባር።

[እ]ርባታ ስ 1. ከብትን የማርባት ስራ። 2. ግስን ወይም አንድን ግሳዊ ቃል በተለያዩ ቅርፆች መተንተን ወይም ማርባት።

[እ]ርባና ([እ]ርባን) ስ ረብ፥ ጥቅም፥ ፋይዳ።

[እ]ርባና ቢስ ጥቅመቢስ፥ ዋጋ የለሽ፥ የማይረባ።

ተራባ ግ 1. እየተዋለደ በዛ፥ ተባዛ። 2. ተስፋፋ፥ ተሰራጨ። 3. (ሰዋ.) በእርባታ ዘዴ ከአንድ ስርወ ቃል ላይ እንደስም፥ ቅፅል፥... ያሉ ውልድ ቃላት ተፈጠሩ።

አረባ ግ 1. ከብትን፥ ዶሮን፥... እየቀለበ በማኖር፥ በማዳቀል፥ በማዋለድ አበዛ። 2. (ሰዋ.) በእርባታ ዘዴ ተጠቅሞ ከአንድ ስርወ ቃል ላይ እንደስም፥ ቅፅል፥... ያሉ ውልድ ቃላትን ፈጠረ።

~አርቢ (ከብትን፥ ዶሮን፥...) እየቀለበ፥ እያዳቀለ፥ እያዋለደ የማስፋፋት፥ የማባዛት ስራ የሚሰራ (ሰው)።

አራባ ግ 1. እያዋለደ አበዛ። 2. አስፋፋ፥ አሰራጨ፥ አዛመተ። *ወሬውን አራባ።* 3. አባዛ። *ፎቶግራፉን አራባ።*

ረባሽ "ረበሸ"ስር ተመ.

ረባዳ ቅ ጎድጓዳ፥ ዝባጣ (መሬት)።

***ረብ**

[እ]ረብ አለ ግ ወደቀ፥ ዘፍ አለ፥ እንዘጭ አለ።

ረብ "ረባ" ስር ተመ.

ረብሸኛ "ረበሸ" ስር ተመ.

ረብሻ ዝ.ክ.

ረብጣ ስ ጥቅል፥ እስር (የገንዘብ፥ የጨርቅ)።

ረታ ግ 1. አሸነፈ፥ ድል ነሳ (በሙግት፥ በክርክር፥ በጦርነት፥...)። 2. ሰላ፥ ተባ፥ ቀና፥ ስለት አወጣ። 3. ተፍታታ፥ ተቃና ተዘረጋ። 4. አንደበቱ ተፍታቶ በጥሩ ሁኔታ ተናገረ።

ተረታ ግ 1. ተሸነፈ፥ ድል ሆነ (በሙግት፥ በክርክር፥...)። 2. ስሜቱ ተሳበ፥ ተመሰጠ ተማረከ። *በፍቅሯ ተረታ።*

ተረታታ ግ ተፍታታ፤ ተዘረጋጋ።

ረከረከ ግ 1. ዝናብ በጣም ጣለ፤ አጨቀየ። *ዝናቡ ሲረከርከው አደረ።* 2. በርክርክ የዜማ ስልት አዜመ። 3. ፅሁፍን አጨማልቆ፤ በሚጭር ፃፈ።

ርክርክ ስ ከያሬዳዊ የዜማ ስልቶች ወይም ምልክቶች አንዱ።

ረከሰ ግ 1. ዋጋው ዝቅ አለ፤ ወረደ። 2. በመጥፎ ስራ ወይም በሃጢአት ላይ ተገኘ። 3. ንፁህነቱን፤ ክብሩን አጣ። 4. ሃይሉ ጠንካሬ፤ ተበላሸ (አስማት፤ መድሃኒት፤...)። 5. ከመብዛቱ ወይም ፈላጊ ከማጣቱ የተነሳ ዋጋ አጣ፤ ወደቀ።

ረኪስ ቅ ዋጋው ያልተወደደ፤ ርካሽ።

ርካሽ ቅ 1. ዋጋው ቀላል፤ ዝቅተኛ የሆነ። 2. በአይነቱና በደረጃው ተራ፤ መናኛ፤ዝቅተኛ የሆነ። 3. ከብቶች ሲበሉ ያዝረከረኩት የድርቆሽ ወይም የገለባ ትርፍራፊ።

[እ] ርኩስ ቅ ንፁህ፤ ቅዱስ ያልሆነ፤ ነውረኛ፤ በሃጢአት ያደፈ። 2. አስፀያፊ፤ እንደነውር የሚታይ፤ ሲቀመስ፤ ሲበላ የማይችል። 3. ክፉ፤ የተጠላ፤ ቅን የማያስብ።

[እ] ርኩስ መንፈስ ስ ሰይጣን፤ አጋንንት።

አረከሰ ግ 1. ዋጋን ሰበረ። 2. መጥፎ ስም ሰጠ፤ አንቋሸሸ። 3. የመድሃኒትን ሃይል ቀነሰ።4. ሃጢአት አሰራ፤ አጎደፈ፤ በከለ።

ማርከሻ ስ መድሃኒት ከተወሰደ በኋላ ሰውነት የሚጎዳ ሆኖ ሲገኝ የመድሃኒቱን ሃይል ለመቀነስ ወይም መርዝነቱን ለማፍረስ የሚወሰድ መድሃኒት።

አራከሰ ግ 1. ዋጋ ሰበረ፤ ዋጋ አጣጣ። 2. አጥላላ፤ አንቋሸሸ።

*ረከበ^1

ሩካቤ [ስጋ] ስ ፍትወተ ስጋ፤ የወንድና የሴት የግብረስጋ ግንኙነት።

ተራክቦ ስ 1. የወንድና የሴት በግብረ ስጋ መገናኘት። 2. ግንኙነት።

*ረከበ^2

ርክክብ ስ የመቀበልና የመስጠት ክንውን።

ተረከበ ግ ተቀበለ፤ ወሰደ፤ በእጅ አደረገ።

ተረካቢ ስ በአስረካቢ እጅ የነበረን እቃ ወይም ስራ የሚቀበል ወገን፤ ተቀባይ ክፍል።

ተረካከበ ግ ተረካቢ ከአስረካቢ ተቀበለ፤ ወሰደ (እቃን፤ ስራን፤...)።

አረካከበ ግ በተረካቢና በአስረካቢ መካከል የሚካሄደውን የርክክብ ስራ መራ፤ እንደታዛቢ ወይም እንደ ምስክር ሆኖ ተመለከተ።

አረካካቢ ስ የርክክብን ስራ ወይም ክንውን የሚቆጣጠር፤ በምስክርነት የሚመለከት ግለሰብ ወይም አካል።

አስረከበ ግ በይዞታ የነበረውን እቃ ወይም ንብረት፤... ለተረካቢው ወገን ሰጠ።

አስረካቢ ስ በይዞታው ስር የነበረውን እቃ፤ ንብረት፤... ለተረካቢ የሚሰጥ፤ የሚያስተላልፍ ግለሰብ ወይም ድርጅት።

ረከቦት ስ ከእንጨት፤ ከብረት፤... የተሰራና ቡና በሚቀዳበት ጊዜ ስኒ የሚደረደርበት እቃ።



ረከቦት

*ረከፈከፈ

[እ] ርክፍካፌ ስ ካፊያ። *በሃምሌ ወጨፎ በሰኔ ርክፍካፌ።*

ተርከፈከፈ ግ 1. ተረጨ። 2. ተንዠንዠ፤ ተረበረበ። 3. ጥቂት ጥቂት ተዳረሰ፤ ትንሽ ትንሽ ተሰጠ።

አርከፈከፈ ግ 1. ረጨ። 2. አካፋ፤ አንጠባጠበ። 3. ጥቂት ጥቂት አዳረሰ። 4. ረበረበ፤ ንዠንዠ።

ረኪስ "ረከሰ" ስር ተመ.

ረካ ግ 1. ጠጥቶ ጠገበ፤ ጥሙን ቆረጠ። 2. የልቡ ደረሰ፤ የሚፈልገውን በማግኘቱ ተደሰተ።

[እ]ርካታ ስ የፈለጉትን በአጥጋቢ ሁኔታ በማግኘት፤ በማድረግ፤... የሚገኝ ደስታ።

አረካ ግ 1. አጠገበ። 2. የልብ አደረሰ፤ አስደሰተ።

አርኪ ቅ አጥጋቢ፤ የልብ የሚያደርስ።

*ረከተ

ርኩቻ ስ የአካል ወይም የአስተሳሰብ ግጭት፤ ፍትጊያ፤ ጥል።

ተራኮተ ግ 1. ተጣላ፤ ተማታ፤ ተደባደበ። 2. ተሻማ፤ ተናነቀ፤ አንድን ነገር ለማግኘት፤ ለመውሰድ ተጋፋ። 3. ተሟገተ፤ ተከራከረ፤ ተጨቃጨቀ።

አራኮተ ግ 1. አጣላ፤ አማታ፤ እርስ በርስ አደባደበ። 2. አሻማ።

*ረወጠ

ተራወጠ ግ ተሯሯጠ፤ ወዲያ ወዲህ ሄደ፤ ኳተነ።

አራወጠ ግ 1. አባረረ፥ አሯሯጠ። 2. አስፋ፥ አዋከበ፡ ወዲያ ወዲህ አሳደፈ።

ረዘመ ግ ተመዘዘ፡ አደገ፥ በቁመት ከፍ አለ። 2. በለጠ። 3. በዛ፥ ከሚፈለገው ወይም ከልክ በላይ ሆነ። 4. ተንተተ፥ ተንዛዛ። *የስራ አስኪያጁ ንግግር ረዘመ።* 5. ብዙ ቆየ። *እድሜው ረዘመ።*

ረዥም "ረጅም"ን ተመ.

ረጅም(ረዥም) ቅ 1. ቁመቱ ትልቅ የሆነ፥ ዘለግ ያለ። 2. የተንዛዛ። 3. ብዙ የሚቆይ (የቆየ)። *የሊቀው አገልግሎት ረዥም ነው።*

ለረጅም ጊዜ ለብዙ ጊዜ።

በረጅሙ ተጣራ ጮክ ብሎ፥ ድምፁን ዘለግ አድርጎ ጠራ።

በረጅም ጊዜ የሚከፈል ቀስ በቀስ፥ ጊዜ ወስዶ የሚከፈል።

ከረጅሙ በአጭሩ አንድን ሃሳብ ከብዙ በጥቂቱ ለማቅረብ ሲፈለግ በማያያዣነት ወይም በመንደርደሪያነት የሚያገለግል ሃረግ። *ከረጅሙ ባጭሩ ሁኔታውን እንደሚከተለው አቀርባለሁ።*

ረጅሜ ስ ረዘም ያለው የዶሮ ቅልጥም(ስእሉን የዶሮ ብልት ስር ተመ.)።

ረጅም ልቦለድ ስ (ስነ.ፅ.) በርከት ያሉ ገፀባህርያትና ውስብስብ ታሪኮችን በአንድነት አስተሳስሮ ይዞ የሚጓዝና የፈጠራ ስራ የሆነ፥ በስድ ንባብ የተቀነባበረ የስነ ፅሁፍ ዘርፍ።

ርዝመት ስ 1. በቁመት ትልቅ መሆን። 2. የቁመት ወይም የርቀት መጠን።

ርዝመት አለው በቁመቱ ትልቅ፥ ረጅም ነው።

ርዝማኔ ስ የቁመት መጠን።

ተራዘመ ግ 1.ለሌላ ጊዜ ተላለፈ (ለምሳሌ ቀጠሮው)። 2. ኮንትራቱ፥ የስራ ውሉ፥... ቀጠለ፥ የጊዜ ወሰኑ ጨመረ። 3. የጊዜ መጠኑ ወይም ቆይታው ጨመረ፥ ከፍ አለ።

አረዘመ ግ 1. ከፍ አደረገ (በቁመት)። 2. አንተተ፥ አንዛዛ (ነገርን)። 3. ብዙ ጊዜ ወይም ዘመን አቆየ። *እድሜውን አረዘመ።*

አራዘመ ግ 1. ለሌላ ጊዜ አስተላለፈ። 2. (የውሉን፥ የኮንትራትን፥...) የቆይታ ጊዜ ጨመረ። 3. የጊዜ መጠኑን ወይም ቆይታውን ጨመረ፥ ከፍ አደረገ።

አስረዘመ ግ 1. (በቁመት) ከፍ አደረገ። 2. አንተተ፥ አንዛዛ (ነገርን)። 3. አረዘመ (እድሜን)።

ረዳ ግ 1. በገንዘብ፥ በቁሳቁስ፥ በስራ፥ በጉልበት፥ በሃሳብ፥... አገዘ። 2. በመድሃኒትነት፥ በመፍትሄነት፥... አገለገለ። *መድሃኒቱ ለራስ ምታት ይረዳል።*

ርዳ ተራዳ ተጋገዘ፥ ተደጋገፈ፥ ተባበረ።

ረዳት ስ 1. አንድን ሰው በተለያዩ መንገዶች የሚያግዝ፥ የሚረዳ ሰው፥ አጋዥ፥ ደጋፊ። 2. በትላልቅ ወይም በንግድ መኪናዎች ላይ ለመኪናው ውሃ፥ ናፍታ፥ ዘይት የመሙላቱን፥ ሸራ የማልበሱን፥... ስራ የሚሰራ ሰው። ቅ 3. የበላይ ሃላፊውን በስራ የሚያግዝ ወይም የሚረዳ።

ረድ (ረድእ) ስ በገዳም ውስጥ አቅመ ደካማ መነኮሳትን የሚያገለግል ሰው።

ረድኤት (ረዴት) ስ 1. በረከት። 2. እርዳታ።

አርድእት በፊደል ተራው ተመ.

[እ]ርዳታ ስ የገንዘብ፥ የቁሳቁስ፥ የጉልበት፥ የሃሳብ፥... እገዛ፥ ድጋፍ።

የ[እ]ርዳታ ድርጅት ስ እርዳታን የሚሰጥ ወይም የሚለግስ በጎ አድራጊ ድርጅት።

ተረዳ ግ እርዳታ አገኘ፥ ተሰጠው።

ተረጂ ስ በሌሎች እርዳታ የሚኖር ሰው። 2. ድጋፍ ወይም እርዳታ ተቀባይ።

መረዳጃ ቅ እርዳታን፥ ድጋፍን (ለአባላቱ) የሚሰጥ፥ የሚያስተባብር ማህበር፥ ተቋም፥...።

መረዳጃ ማህበር ስ እርዳታን፥ ድጋፍን (ለአባላቱ) የሚሰጥ ወይም የሚያስተባብር ማህበር፥ ተቋም።

ተራዳ ግ ረዳ፥ አገዘ።

ተራድኦ ስ የመረዳዳት ወይም እርዳታ የመስጠት ተግባር።

²ረዳ

መርዶ ስ 1. የዘመዱን፥ የወዳጁን፥... መሞት እንዲሰማና እርሙን እንዲያወጣ ለሟች ዘመድ ወይም የቅርብ ወዳጅ የሚነገር የሞት ዜና። 2. አሳዛኝና አስደንጋጭ ዜና።

ተረዳ ግ 1. ተገነዘበ አወቀ። 2. የቅርብ ዘመዱን ወይም ወዳጁን ሞት ሰማ።

መረጃ ስ 1. ስለ አንድ ነገር የሚሰጥ ማብራሪያ ወይም መግለጫ። 2. የትምህርት፥ የስራ፥ የተሰጥኦ፥... ማስረጃ ወይም የምስክር ወረቀት። 3. አንድ ነገር መሆን አለመሆኑን ወይም መደረግ አለመደረጉን የሚጠቁም፥ የሚያሳይ የፅሁፍ ወይም የቃል ማስረጃ። 4 የመንግስት የስለላ ድርጅት።

አረዳ ግ መርዶ ነገረ።

አስረዳ ግ ገለፀ፥ አብራራ፥ አሳወቀ፥ አስገነዘበ።

ማስረጃ ስ 1. ምስክር። 2. የአንድ ነገር ማረጋገጫ ሰነድ ወይም የምስክር ወረቀት።

አስረጅ ስ 1. በአንድ ጉዳይ ላይ ማብራሪያ የሚሰጥ ሰው። 2. እንደምሳሌነት፥ እንደ ምስክርነት፥ እንደማብራሪያ የሚያገለግል ወይም

የሚቀርብ ነገር።

ረዳት " **ረዳ**" ስር ተመ.

ረድ ገ.ከ.

ረድኤት ገ.ከ.

ረድፍ ስ ሰዎች ወይም ሌሎች ነገሮች የተደረደሩበት፣ የተሰለፉበት መስመር።

ረጅሜ "**ረዘመ**" ስር ተመ.

ረጅም ገ.ከ.

ረገመ ግ "እንዲህ ይድረስብህ"፣ "እንዲህ ያድርግህ"፣ "እንዲህ ሁን" እያለ አወገዘ፤ በሌላው ላይ አንዳች መጥፎ ወይም ክፉ ነገር እንዲደርስ ተመኘ።

መርገም ስ የወር አበባ (ብዙውን ጊዜ የመፅሃፍ ቅዱስ አጠቃቀም)።

[እ]ርጉም ቅ ከይሲ፣ ያልተባረከ፣ ክፉ።

[እ]ርግማን ስ በሌላው ላይ ክፉ ነገር እንዲደርስ ተብሎ የተነገረ መጥፎ ምኞት፣ ውግዘት።

የተረገመ ቅ መጥፎ፣ ክፉ (ሰው)።

ተራገመ ግ ረገመ።

*ረገረገ

ረግረግ ስ ውስጡ ውሃ ያለበትና ሲረግጡት ስምጥ ስምጥ የሚል መሬት።

የረግረግ ወፍ ስ ሙሉ ለሙሉ ጥቁር ሆና ግንባሯ ነጭ የሆነ፣ በረግረግ ቦታዎች የምትኖር፣ ሴት ዶሮ የምትመስልና የምትከል ወፍ(ስእሉን ወፍ ስር ተመ.)።

ተረገረገ ግ ነጠር ነጠር እያለ የኩራት አካሄድ ሄደ።

ተረገረገብኝ ተግቢ ከልሆኑ ንግግር ጋር የተያያዘ፤ የንትትና የቁጣ አካላዊ እንቅስቃሴ አሳየን፤ ተንቀነቀብኝ።

አረገረገ ግ ወደላይና ወደታች ተንቀሳቀሰ፣ ተወዛወዘ (ምቾት ለመስጠት ወይም ቀብቶት በማሻት ወይም በመበላሸት፤ ለምሳሌ የሸበ አልጋ፣ የእንጨት ድልድይ ....)።

አረግራጊ ቅ ምቾት ያለው፣ የሚያረገርግ (አልጋ፣ መኪና፣...)።

ረገበ ግ 1. የተወጠረው፣ የጠበቀው ላላ ወይም ለቀቅ አለ። *የአልጋው ሸቦ ረገበ።* 2. በረደ፣ ቀዘቀዘ (የመርነት፣ የጠብ፣... ውጥረት)።

*ረገበ

[እ]ርግብግቢት ስ በተለይ በህፃናት አናት ላይ ከፍ ዝቅ እያለ በትርታ አይነት ሲንቀሳቀስ የሚታይ ከግንባር ከፍ ብሎ የሚገኝ የሰውነት ክፍል።

[እ]ርግብግብ ቅ ርቀቱ፣ ቁመቱ የሌለው ዝቅጥቅጥ።

ተራገበ ግ 1. በማራገቢያ አማካኝነት ነፋስ እንዲያገኘው ተደረገ። *ካልተራገበ ከሰሉ አይቀጣጠልም።* 2. (ዘይ.) ተሟሟቀ፣ ተናፈሰ፣ እንዲጋጋል ተደረገ (ጠቡ፣ ወሬው)።

ተርገበገበ ግ 1. ተወዛወዘ፣ ተውለበለበ። 2. በማራገቢያ አማካኝነት ነፋስ እንዲያገኘው ተደረገ። 3. ተንሰፈሰፈ፣ ራደ፣ ተንቀጠቀጠ። 4. (ዘይ.) ተጨነቀ፣ ተሸቆጠቆጠ።

አራገበ ግ 1.ምልክት ለማሳየት አውለበለበ (ጨርቅን፣ መሃረብን፣...)። 2. በማራገቢያ ነፋስ ሰጠ። 3. (ዘይ.) አባባሰ፣ አጋጋለ (ነገርን)።

ማራገቢያ ስ 1. እሳትን ለማቀጣጠል ወይም እብቅን ከፍሬ በነፋስ ግፊት አማካይነት ለመለየት፣... እንዲረዳ በሰሉ የተዘጋጀ ሰሌን፣ ቆዳ፣ ማርገብገቢያ። 2. በእግር ኳስ ጨዋታ ላይ ጥፋት ሲሰራ የመስመር ዳኛው ምልክት የሚሰጥበት ጨርቅ።

አራጋቢ ስ በእግር ኳስ ጨዋታ የዋናው ዳኛ ረዳት፣ የመስመር ዳኛ።

አርገበገበ ግ 1. አወዛወዘ፣ አውለበለበ። 2. አንሰፈሰፈ፣ አንቀጠቀጠ። 3. (ዘይ.) አስጨነቀ፣ አሸቆጠቆጠ።

ማርገብገቢያ ስ አየር ወደ እሳት አቅጣጫ እንዲንቀሳቀስ የሚገፋና እሳትን ለማቀጣጠል፣ እንዲሁም ሞቃታማ አየርን ወዲያና ወዲህ በፍጥነት በማንቀሳቀስ የሙቀቱን ሃይል ለመቀነስ የሚረዳ ከሰሌን፣ ከሳር፣... የሚሰራ እቃ፤ ማራገቢያ።

ረገዘ

[እ]ርጉዝ ቅ የፀነሰች፣ ያረገዘች (ሴት)፤ ነፍሰጡር።

እርግዝና ስ ፅንስ መያዝ፣ ማርገዝ።

ተረገዘ ግ ተፀነሰ፣ በማህፀን ውስጥ ተቋጠረ (ሽሉ)።

አረገዘ ግ በውስጡ ያዘ፣ አዘለ። *ደመናው ዝናብ አረገዘ /ሰውየው በልቡ ነገር አርግዟል።*

አረገዘች በማህፀኗ ሽል ቋጠረች፣ ፀነሰች።

አስረገዘ ግ እንድትፀነስ፣ እንድታረግዝ አደረገ (በግብረስጋ ግንኙነት)።

ረገደ ግ 1. ተንቀጠቀጠ፣ ተንዘፈዘፈ፣ ራደ። *ከህመሙ የተነሳ ሰውነቱ ረገደ።* 2. ዘለለ፣ ጨፈረ፣ መሬት እየደቃ አለቀሰ።

ርግዶ (ረግዶ፣ ረገዳ) ስ በለቅሶ ጊዜ ከሃዘን የተነሳ የሚደረግ ዝላይ፣ ጭፈራ።

ተርገደገደ ግ አቅም ከማጣት የተነሳ ተንገዳገደ።

አረገደ ግ 1. አቅም ከማጣት የተነሳ ተንቀጠቀጠ፣ ተብረከረከ። 2. እየዘለለ፣ ደረት

እየመታ አለቀሰ። 3. (ዘይ.) ተሽቆጠቆጠ፣ ተለማመጠ፣ ሽርጉድ አለ። *ላለው ቅንጭብ ያረግዳል።*

ማርገጃ ስ ከቤተክርስቲያን ቅፅረ ግቢ ውጪ የሚገኝ የሟች ዘመድና ወዳጅ ደረት እየመቱና እየዘለሉ የሚያለቅሱበት ክልል ወይም ቦታ።

አርጋጅ ስ ደረት እየመታና እየዘለለ ለሞተ ዘመድና ወዳጅ የሚያለቅስ ሰው።

አርገደገደ ግ አንገዳገደ።

አስረገደ ግ አስፈራ፣ አሽቆጠቆጠ፣ አንቀጠቀጠ።

ረገድ ስ 1. አኳያ፣ በኩል። *በትምህርት ረገድ አገራችን ከፍተኛ ጥረት ታደርጋለች።* 2. አቅም፣ መጠን። *በተቻለ ረገድ ልረዳህ እሞክራለሁ።*

ረገጠ ግ 1. በእግር ደቀደቀ፣ ጠቀጠቀ፣ ረመረመ። 2. መታ፣ ደበደበ፣ ቀጠቀጠ። 3. እግሩን አሳረፈበት፣ በእግሩ ተጫነ፣ በላዩ ላይ ቆመ። *እግሬን ረገጠኝ።* 4. በእግር አሸ (ቆዳን፣ ስልቻን፣ ዝተትን፣...)። 5. (ለቤት መምረጊያ የሚሆን ጭቃን ከጭድ ጋር) አቦካ። 6. ጨፈረ። 7. ናቀ፣ ደፈረ፣ ጥሶ ሄደ (ሰበሰበን፣ ማእድን)። 8. ከለለ (ድንበርን)። 9. ሰረረ፣ መታ (ፈረስ፣ አህያ)።

ረግጦ ገዛ በጭቆና አስተዳደረ።

መርገጥ ስ ወገልንና ሞፈርን የሚያያይዝ ጠፍር ወይም ገመድ (ስእሉን ሞፈር በር ተመ.)።

መርገጫ ስ 1. በወረቀት ላይ ያረፈ ቀለምን ለማምጠጫ የሚያገለግል የፅህፈት መሳሪያ። 2. ማህተምን ወይም የጣት አሻራን ለፊርማ ቀለም የሚያስነኩበት የቀለም መደብ።

ረጋጭ ስ ሰልፍ የሚማር ምልምል ወታደር።

[እ]ርጋጭ ቅ በከብቶች እግር እየተረገጠ የቆሸሸና መጥፎ ጣእም ያለው (ውሃ፣ ሳር፣...)።

[እርግጫ ስ 1. ዱካ፣ ኮቴ፣ ፈለግ። 2. እግርን አንስቶ በመማታት የሚጫወቱት የልጆች ጨዋታ። 3. ልፊያ። 4. የወታደር የሰልፍ ትምህርት።

ተራገጠ ግ 1. በእርግጫ መታ፣ ተማታ። 2. ተላፋ፣ ተዘለለ።

ተራጋጭ ቅ የመራገጥ አመል ያለበት(በብዙውን ጊዜ ለከብት)።

ተረጋገጠ ግ በእግር ተረመረመ።

መረጋገጫ ስ 1. መረማመጃ፣ መተላለፊያ መንገድ። 2. መወጣጫ እርከን፣ ደረጃ።

አስረገጠ ግ አሸበሸበ። *መዘምራኑ ለማስረገጥ ተዘጋጅተዋል።*

አስረጋጭ ስ አሽባሽቢ (ደብተራ፣ ካህን)።

*ረገጠ

[እ]ርግጥ ቅ ትክክል፣ የማያጠራጥር፣ ሃቅ ወይም እውነት የሆነ።

[እ]ርግጠኛ ቅ 1. ትክክለኛ፣ የማያጠራጥር፣ እውነተኛ። 2. ጥርጣሬ የሌለው፣ የሚተማመን፣ በትክክል የሚያውቅ። *እኔው ይሄ ለመሆኑ እርግጠኛ ነኝ።*

ተረጋገጠ ግ 1. ትክክል መሆኑ፣ እውነቱ ወይም ሃቁ ታወቀ። 2. እውን ሆነ፣ በተግባር ተተረጎመ።

አረጋገጠ ግ 1. እውነት መሆኑን አጣራ፣ አወቀ። 2. እውነት ወይም ትክክል መሆኑን አሳወቀ፣ መሰከረ። 3. እውን አደረገ፣ በተግባር ላይ አዋለ።

አስረገጠ ግ እውነት ወይም ትክክል መሆኑን፣ አጣራ፣ አወቀ። *አስረግጠህ ተናገር።*

ረገፈ ግ 1. ከነበረበት ወደታች ወረደ፣ ወደቀ፣ ተንጠባጠበ። 2. ጠፋ፣ ዳነ (የኩፍኝ፣ የፈንጣጣ፣... ቁስል)። 3. ወለቀ፣ ተነቀለ (ጥርስ)። 4. (ዘይ.) ሀ.አለቀ፣ ሞተ። *ብዙ ሰው ረገፈ።* ለ.ጠፋ፣ በነነ። *ሀብቱ ረገፈ።*

መርገፍ ስ በድባብ፣ በጃንጥላ፣ በቤተክርስቲያን ጉልላት፣ በመሶበወርቅ ወይም በበቅሎ እቃ ላይ የሚደረግ ዘርፍ፣ እሚዋች ጌጥ።



ርጋፊ ቅ 1. የወደቀ፣ የተንጠባጠበ (ፍራፍሬ ወይም ሌላ ነገር)። 2. የመጨረሻ፣ እላቂ፣ ሙጣጭ (እህል፣ ዱቄት፣...)። 3.(ዘይ.) የተጣለ፣ የማይረባ፣ ደህ ነው የማይባል፣ ውዳቂ።

ርጋፎ ዝ.ከ.

[እ]ርግፍ [እ]ርግፍ አለ ግ 1. ፈሰሰ፣ ዱብዱብ አለ (ለምሳሌ እንባ)። 2. ረገፈ።

[እ]ርግፍ አደረገ ግ 1. ፈፅሞ፣ ጨርሶ ተወ። 2. ሙጥጥ አድርጎ ጨረሰ።

ተራገፈ ግ 1. ተወገደ (ቆሻሻ)። 2. ባዶ ሆነ፣ ተሟጠጠ። 3. ወረደ (ጭነት ወይም ተሳፋሪ)።

አራገፈ ግ 1. አወለቀ፣ ነቀለ (ጥርስን)። 2. አወረደ (ጭነትን፣ ተሳፋሪን)። 3. አስወገደ

(ቅጠሉን)። 4. ጨረሰ፡ አሟጠጠ።

*ረገፈገፈ

[እ]ርግፍግፍ አለ ግ ተርገፈገፈ።

ተርገፈገፈ ግ ተንቀጠቀጠ፡ ተንዘፈዘፈ።

አርገፈገፈ ግ አንቀጠቀጠ፡ አንዘፈዘፈ፡ ነቀነቀ።

ረጋ

ረጋ ሰራሽ ቅ አዋቂ ወይም ባለሙያ ያልሰራው እቃ።

ረጋ ግ 1. ቆመ፡ ፀና። 2. ወፈረ፡ ተጋገረ፡ ለደለደ። 3. ፀጥ አለ፡ በረደ፡ ሰላም ሰፈነ።

ይርጋ ስ (ህግ) በፍርድ ቤት የሚነሱ ክርክሮች በህግ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ መቅረብ እንደሚገባቸውና ጉዳዮቹ በተቆረጠው የጊዜ ገደብ ካልቀረቡ በጉዳዮቹ ላይ ክስ ማቅረብ አለመቻሉን፡ ክሱም ቀሪ መሆኑን የሚያመለክት ሁኔታ።

እርጋታ ስ ዝግታ፡ ቀስታ፡ የሰከነ ሁኔታ።

እርጎ ስ የረጋ ወተት።

ረጋ አለ 1. አደብ ገዛ፡ መንቀዥቀዥ ተወ፡ ሰከነ፡ ጨመተ። 2. ጋብ፡ ቀዝቀዝ አለ።

ተረጋጋ ግ 1. ፀጥ አለ፡ በረደ (ረብሻ፡ ሁከት)። 2. ተፅናና፡ ተበረታታ፡ የመንፈስ እረፍት አገኘ።

አረጋ ግ 1. አቆመ፡ አሳረፈ። 2. አፀና፡ አፀደቀ።

አረጋጋ ግ 1. ሁከትን አበረደ፡ ሰላም አሰፈነ። 2. አፅናና፡ አበረታታ፡ የአእምሮ እረፍት ሰጠ።

ረጋጭ "ረገጠ" ስር ተመ.

ረግረግ "*ረገረገ" ስር ተመ.

ረግዶ "ረገደ" ስር "ርግዶ" ን ተመ.

ረጠበ¹ ግ ራሰ፡ ረሰረሰ።

[እ]ርጥብ ቅ 1. የራሰ፡ የረሰረሰ። 2 ለምለም 3. ያልደረቀ። 4. (ዘይ.) ሞኝ፡ ያልበሰለ (ሰው)።

[እ]ርጥብ ልጅ ስ ያልጠና፡ ያልጠነከረ፡ አራስ ልጅ፡ ጨቅላ።

[እ] ርጥብ ሬሳ ስ ሞቶ ያልቆየና ያላደረ፡ ትኩስ ሬሳ።

[እ] ርጥብ ስጋ ስ ያልተጠበሰ ወይም ያልተቀቀለ፡ ትኩስ ጥሬ ስጋ።

[እ] ርጥብ አራስ ስ በቅርብ ቀን የወለደች ሴት።

[እ] ርጥብ እማኝ ስ በሸንጎ ላይ የሚነሳ አዲስ ተጨማሪ ምስክር።

[እ] ርጥበት ስ በፈሳሽ ነገር የመራስ ሁኔታ፤ በላዩ ወይም በውስጡ ያለው ፈሳሽ።

አረጠበ ግ 1. ውሃ ወይም ሌላ ፈሳሽ ነገር አስነካ። 2. አራሰ፡ አረሰረሰ።

አራጠበ ግ ልትወልድ የደረሰች ሴት በምጥ ሰአት ላይ የእንሽርት ውሃዋ ፈሰሰ።

ረጠበ² ግ የተቸገረን ለመርዳት፡ የጠፋን ለመተካት የገንዘብ ወይም የእቃ ስጦታ አደረገ፤ እርዳታ ሰጠ።

እርጥባን ስ እርዳታ (የገንዘብ፡ የእቃ)።

ተረጠበ ግ እርጥባን ተሰጠው፡ ተቀበለ።

ተረጣቢ ቅ ገንዘብ ተረጂ።

ረጠጠ ግ አመቀ፡ ተጫነ (የሚሰፈር እህልን)።

ርጥ ስ አነባበሮ (ድልህ፡ በሲጥ፡ ኑግ፡ ተልባ ያለበት)።

[እ] ርጥጥ ቅ 1. እምቅ። 2. (ዘይ.) ውዝፍ።

ተረጠጠ ግ 1. ታመቀ። 2. (ዘይ.) ስራ ፈትቶ፡ ተውዘፎ ተቀመጠ።

እርጧጧ ቅ 1. ሰነፍ፡ ውዝፍ፡ ከተቀመጠበት የማይነሳ (ሰው)። 2. ቁመተ ረዥም፡ በገርዷ ሰፊ የሆነች (ሴት)።

ረጨ ግ 1. ፈነጠቀ፡ አርከፈከፈ። 2. ነዛ፡ በተነ፡ ዘራ። 3. አስራጨ፡ አደረሰ። 4. (ዘይ.) አባከነ (ገንዘብን)።

ተረጨ ግ ተፈነጠቀ፡ ተርከፈከፈ (ለምሳሌ ውሃ፡ ጠበል)።

ተራጨ ግ ረጨ፡ ፈሳሽን ፈነጠቀ (ሌላ ሰው ላይ ወይም እርስ በራሱ)።

ረጨት ስ የቡሆ እቃ እጣቢ፡ ልቅላቂ።

ረፈረፈ ግ 1. ጣለ፡ ለሸለሸ፡ አሰተኛ፡ አጋደመ። 2. (ዘይ.) በብዛት ገደለ፡ ጨፈጨፈ።

ረፍረፍ ስ ሽሩባ ያልተሰራ ወይም ያልተቆሸጠ የሴት ፀጉር፡ ጎፈሬነት ያለው።

ተረፈረፈ ግ ወደቀ፡ ተጋደመ፡ ተኛ (በእንቅልፍ፡ በበሽታ፡ በሞት፡ ...)።

*ረፈቀ

ምርፋቅ ስ 1. በቤተክርስቲያን ቅጽ በቤተልሔም አጠገብ ካህናት ተረፈ መስዋእት ለመመገብ የሚቀመጡበት ስፍራ። 2. በገዳም የሚኖሩ መነኮሳት በህብረት የሚመገቡበት ቤት፡ የምግብ አዳራሽ፤ ቤተምርፋቅም ይባላል።

አረፈቀ ግ 1. አቅም አጣ፡ ደከመ፡ ተኛ፡ ወደቀ። 2. እቤት ዋለ፡ ደከመ (ሽማግሌ)።

ረፈደ ግ 1. ከንጋት ቆየ፡ ከጧትነት አለፈ፡ ረፋድ ሆነ። 2. ከሚፈለገው ወይም ከተወሰነው ሰአት በላይ አለፈ፡ ዘገየ።

ረፋድ ስ ጥዋት ከሰባት እስከ አምስት ሰአት

ድረስ ያለው ጊዜ።

አረፈደ ግ ዘገየ፤ ቆየ፤ የተወሰነውን ሰአት አሳለፈ።

አርፋጃ ስ ረፋድ።

አርፋጅ ቅ የተወሰነውን ሰአት አሳልፎ የሚመጣ፤ የሚዘገይ።

ረፍረፍ "ረፈረፈ" ስር ተመ.

ሩ የ"ረ" ፊደል ካእብ ዘር።

ሩህ ስ ነፍስ።

ሩህሩህ "ራራ" ስር "ርህሩህ" ን ተመ.

ሩሎ ስ ለመንገድ ስራና ለመሬት መደልደያ (ማስተካከያ) የሚያገለግል ከባድ የሆነ ተንከባላይ የብረት አካል ያለው መኪና፤ ዳምጠው።

ሩሎ

ሩር(እሩር) ስ 1. ከእንጨት ቁራጭ የሚሰራ ድቡልቡል የገና መጫወቻ ኳስ። 2. (ዘይ.፥ ስድብ) አጭር (ሰው)።

ሩቅ "ራቀ" ስር ተመ.

ሩቤኔቶ ስ የቧንቧ መክፈቻና መዝጊያ።

ሩብ (እሩብ) ቅ 1. ከአራት አንድ እጅ፤ አንድ አራተኛ። ስ 2. በቀድሞ ጊዜ የነበረ፥ በጊዜው የብር አንድ አራተኛ ዋጋ የነበረው ገንዘብ።

ሩካቤ [ስጋ] "ረከበ"ስር ተመ.

ሩዝ ስ በአብዛኛው ሞቃት በሆነው የእስያ አህጉር ውስጥ የሚበቅልና የአለም አንድ ሶስተኛው ህዝብ የሚመገበው የእህል አይነት።

ሩጋ ስ የአውሬ መያዣ ወጥመድ።

ሩጫ "ሮጠ" ስር ተመ.

ሪ የ"ረ" ፊደል ሳልስ ዘር።

ሪህ ስ በአካል መጋጠሚያዎች ላይ የሚሰማ የቁርጥማት በሽታ።

ሪቅ ስ ከእንጨትና ከጭቃ የሚሰራ፥ ከላይ ደረብ ያለው የእህል መክተቻ፤ ጎተራ።

ሪከርድ ስ 1. ተመዝግቦ የሚገኝ መረጃ። 2. (ስፖ.) ተመዝግቦ የሚገኝ ከፍተኛ የውድድር ውጤት፥ ነጥብ።

ሪከርድ ሰበረ ቀደም ሲል ተገኝቶ የነበረውን ከፍተኛውን የውድድር ውጤት አሻሻለ።

ሪከርድ አለበት ካሁን በፊት የሰራውና ተመዝግቦ የሚገኝ የወንጀል ድርጊት መረጃ አለበት።

ሪዝ ስ 1. ጢም። 2. ፀጉሩን ተሸልቶ የማያውቅ የበግ ጠቦት። 3. ለመጀመሪያ ጊዜ የተሸለተና ለበርኖስ የሚሆን ለስላሳ የጠቦት በግ ፀጉር።

ሪጋ ስ 1. ተራ፤ ረድፍ። 2. በወርቅ ወይም በሌላ ነገር ላይ በተደጋጋሚነት የተሰመረ መስመር። 3. የልብስ ማስተካከያ ረዥም ማውጫ፤ እንጨት።

ሪፈረንደም ስ ውሳኔ ህዝብ።

ሪፐብሊክ ስ ህዝብ በመረጠው መሪ የሚተዳደር መንግስት፤ ህዝባዊ መንግስት።

ሪፖርተር ስ 1. ሪፖርት የሚያዘጋጅና የሚያቀርብ ሰው። 2. ቃል አቀባይ፥ ዘጋቢ።

ሪፖርት ስ ስለ አንድ ነገር ወይም ሰው የሚሰጥ የፅሁፍ ማብራሪያ፤ መግለጫ፤ ዘገባ።

ራ የ"ረ" ፊደል ራብእ ዘር።

ራሄሎ ስ የዛር ስም (በባላገር እንደወረርሽኝ፡ ጉንፋን ያለ በሽታ በገባ ጊዜ፥ ራሄሎ ይዛልን ትሄዳለችና እንሸኛት በሚል እምነት ንፍሮ ቀቅለውና ራቅ ወዳለ ቦታ ወስደው መንገድ ላይ ይበትኑላታል)።

ራመመ ግ ፈገፈገ፥ አሸ፤ ዳመጠ፥ አለሰለሰ (ብራናን)።

ራመድ አለ "*ረመደ"ስር ተመ.

ራማ ስ (መፅ.ቅ.) ሰማይ።

ራራ ግ የሃዘኔታ፥ የደግነት፥ የመሳሳት ስሜት አሳየ።

ራሮት ስ ሃዘኔታ።

ርህሩህ (ሩህሩህ) ቅ አዛኝ፤ ጨካኝ ያልሆነ።

ርህራሄ ስ ሃዘኔታ፤ ቸርነት፤ ደግነት።

አራራ ግ አዛኝ፤ ርህሩህ አደረገ፤ አሳዘነ፤ ልብ ነካ።

ራሰ ግ ረጠበ፤ ረሰረሰ።

አራሰ ግ 1. አረጠበ፥ አረሰረሰ፤ አበሰበሰ። 2. አረካ፥ አስደሰተ። *ላንጀቱን አራሰው።*

ራስ ስ 1. የሰውና የእንስሳት ሰውነት የላይኛው ክፍል፤ ጭንቅላት፤ አናት፤ አንጎልን የያዘው ክፍለ አካል። 2. የአንድ ነገር ጫፍ፤ ቁንጮ፤ አናት። 3. ከደጃዝማች በላይ ከንጉስ በታች የሆነ የቀድሞ ጊዜ የማእረግ ስም። 4. የማሰብ እኔነት ወይም አንድን ሰው በአፅንኦት ለመጥቀስ ሲፈለግ የሚያገለግል ተውላጠ ስም። *ነገሩን እኔ ራሴ አይቸዋለሁ /አንተ ራስህን ጠብቅ/ ራሳችን በመጣነው ጣጣ ሌላውን ልንወቅስ አይገባም።*



ራስ

ራሱ ዞረ 1. ተናደደ፡ ተበሳጨ። 2. ግራ ገባው፥ ተምታታበት፥ ተደናገረ።

ራሱ ጠና በረታ፥ ሰውነቱ ጠነከረ (ህፃን)።

ራሱን ሳተ ከድካም፥ ከስካር፥ ከበሽታ፥... የተነሳ ዛለ፤ አቅም አጣ፥ ደከመ፤ ራሱን መቆጣጠር አቃተው።

ራሱን ተሳመ እንደዚህ እንደዚህ ያለ ስራ አስብህና ሰው አስተባብረህ ስራውን እንድትረዳኝ ተብሎ ተጠየቀ፥ ልመና ቀረበለት።

ራስ ስሞሽ ስ ሰው አስተባብረህ በተሰወነ ቀን ስራ እንድታግዘኝ የሚል ጥብቅ ልመና፥ ጥያቄ።

ራሱን ቻለ ግ 1. ራሱን በራሱ ማስተዳደር ወይም መርዳት ጀመረ፤ ተቋቋመ። 2. የሌላ እርዳታ ከመሻት ዳነ፤ በረታ፤ ጠነከረ።

ራሱን ነቀነቀ ራሱን በማንቀሳቀስ የዛቻ፥ የማስጠንቀቂያ፤ የእሺታ፤ የእምቢታ፤ የትዝብት፤... ምልክት ሰጠ።

ራሱን አራቀ ተገለለ፥ ብቻውን ሆነ፥ ራሱን ለየ፤ ሸሸ።

ራሱን አሸነፈ የማንንም እርዳታ ሳይሻ ኑሮውን መምራት ቻለ።

ራሱን አወቀ 1. በረታ፤ አቅም አገኘ፤ ራሱን መቆጣጠር ቻለ። 2. ማስተዋል፥ ማመዛዘን ቻለ። 3. ማንነቱን ተረዳ፤ አወቀ።

ራሱን አወጣ 1. ከመጥፎ ነገር ራሱን አዳነ። 2. ተጣጥሮ በኑሮው ደህና ቦታ ደረሰ።

ራሱን አዋረደ 1. በመጥፎ ድርጊት ላይ ተገኘ። 2. ታዛዥ ሆነ (ክብሩን በፈቃዱ ዝቅ በማድረግ)።

ራሱን ገታ አንድን ነገር ከማድረግ ተቆጠበ።

ራሱን ጠበቀ ጤንነቱን ተንከባከበ፤ ራሱን ከአደጋ ወይም ከመጥፎ ነገር አገለለ።

ራሱን ጣለ በኑሮው፥ በአለባበሱ ግዴለሽ ፥ ደንታ ቢስ ሆነ።

ራስ ላይ ወጣ 1. አሰከረ፤ ናላ አዞረ፤ አሳመመ (መጠጥ)። 2. ተንጠባረረ፤ ተንቀባረረ፤ ናቀ፤ ተዳፈረ። 3. በነገር ጠመደ።

ራስ በራስ እናት ባናት፤ ላይ በላይ፤ በተከታታይ። *ራስ በራስ ልጅ ወልዳ ተቸገረች።*

ራስ በራ ቅ በእድሜ ወይም በዘር ምክንያት፥ በከፊል በራሱ ላይ ፀጉር የሌለው።

ራስ ቡሃ ቅ በራሱ ላይ ነጭ እከክ ወይም ቋረቁር ያለበት (ሰው)።

ራስ ክፍት ቅ ብልህ፤ ነገር ቶሎ የሚገባው።

ራስ ዘናና ቅ ራሰ ትልቅ፤ ጭንቅላታም።

ራስ መጠበቂያ ስ 1. ጠበንጃ፤ ጩቤ፤ ዱላ የመሳሰለውና ራስን ከወንበዴ ወይም ከአደጋ መከላከያ መሳሪያ። 2. ለክፉ ጊዜ የሚያስቀምጡት ገንዘብ።

ራስ ማሰሪያ ስ ሻሽ።

ራስ ምላስ ስ የተቀቀለ የበግ ጭንቅላት ከነምላሱ።

ራስ ምታት ስ የራስ ህመም በሽታ።

ራስ ሰሪ ስ ፀጉር የምትሰራ ሴት፤ ቆናጅ።

ራስ ቁር ስ የጥንት ጦረኛ ከራሱ ላይ የሚያደርገው የራስ መከላከያ ቆብ።

ራስ ክምር ስ ራሱ ክብና ጠፍጣፋ የሆነ የእፅዋት አይነት፤ የፈረስ ዘንግም ይባላል።

ራስ ወርቅ ስ በጥንት ጊዜ የራስነት ማእረግ የተሰጠው ሰው ራሱ ላይ ያደርገው የነበረ ከወርቅ የተሰራ የራስ ቁር አይነት ቆብ፤ አክሊል።

ራስ ወዳድ ቅ ለራሱ እንጂ ለሌሎች የማያስብ፤ ይሉኝታ ቢስ።

ራስጌ ስ በመኝታ ጊዜ ራስ ወይም ጭንቅላት የሚውልበት ወይም የሚያርፍበት ቦታ፤ አቅጣጫ፤ ትራስጌም ይባላል።

የራስ የግል።

እየራሱ እያንዳንዱ።

[የ]ራስ ቅል ስ አንጎልን አቅፎና ሸፍኖ የያዘው የራስ አጥንት።

የራስ ቅማል ስ በራስ ጠጉር ውስጥ የሚገኝ ወይም የሚፈጠር ጥቁር ቅማል።

ራሽን ስ 1. በጦርነት፤ በድርቅ፤... አደጋዎች ጊዜ ለእያንዳንዱ ሰው ለተወሰነ ጊዜ እንዲያገለግል የሚታደል ምግብና መጠን የመሳሰለ የፍጆታ እቃ። 2. ለወታደሮች፤ ለተማሪዎች፥... ለተወሰነ ጊዜ እንዲያገለግል የሚታደል የምግብ፥ የመጠጥ አቅርቦት፤ ቀለብ።

ራሽን ካርድ ስ በራሽን መልክ የሚሰጡ ነገሮች የሚመዘገቡበት ካርድ፤ የመሸመቻ ካርድም ይባላል።

ራቀ ግ 1. ቅርብ ሳይሆን ቀረ፤ በቀላሉ የማይደረስበት ፥ ሩቅ ሆነ። 2. ረዘመ፥ የሚዘገይ ሆነ (የጊዜ)። 3. ተለየ። *ልጁ ከዘመድ ራቀ*። 4.

ቀው፡ ተገለለ። *ከመጠጥ ራቀ።* 5. በተወሰነ የቦታ ርቀት ወይም ርዝመት ላይ ሆነ፡ ተገኘ። *ጽሕፈት ቤቱ ከዚህ ሳምስት መቶ ሜትር ይርቃል።*

ራቀው ሸሸው፡ አጣ። *ገንዘብ ራቀው /ሰላም ራቀው።*

ሩቅ ቅ ቅርብ ያልሆነ።

ሩቅ ምስራቅ ስ የምእራብ እስያ፡ ቻይና፡ ጃፓንና በአጠገቡ ያሉት ደሴቶች ጭምር አጠቃላይ መጠሪያ።

ሩቅ ሙዱቅ ቅ ከፈጣሪ የራቀ፡ እንጠርጣሪ የወደቀ (ዲያብሎስ)።

[የ]ሩቅ ዘመድ ስ ራቅ ያለ የደም ግንኙነት ወይም ዝምድና ያለው ሰው።

ርቀት ስ 1. ሩቅነት፡ ቅርብ ያለመሆን። 2. ከአንድ ቦታ እስከ ሌላው ያለው የርዝመት ወይም የመራራቅ መጠን።

ርቀት አለው ቅርብ አይደለም፡ ሩቅ ነው።

ተራራቀ ግ 1. ሩቅ ለሩቅ ሆነ፡ ቅርበት አጣ። 2. ተለያየ፡ ተነጣጠለ። 3. ከመቀያየም የተነሳ የማይደራረሱ ሆኑ።

አራቀ ግ 1. ሩቅ አደረገ። 2. ነጠለ፡ ለየ። 3. አገለለ።

አርቆ አሳቢ /ተመልካች ቅ አስተዋይ፡ ለወደፊቱ ጭምር የሚያስብ።

አራራቀ ግ 1. ሩቅ ለሩቅ አደረገ። 2. አለያየ፡ ነጣጠለ። 3. አቀያየመ።

አራርቆ ወለደ አከታትሎ ሳይሆን እየቆየ፡ ጊዜ እየሰጠ ወለደ። *አራርቆ መውለድ ለቤተሰብ ምጣኔ ይረዳል።*

***ራቆተ**

ራቁት ቅ 1. ልብስ ወይም ሽፋን የሌለው፡ እርቃኑን። 2. ባዶ። *ራቁት እንጀራ።*

ራቁቱን አስቀረው ሙልጭ አድርጎ ወሰደበት (ልብሱን፡ ንብረቱን)።

ተራቆተ ግ 1. መለመላውን ወይም ራቁቱን ሆነ። 2. ባዶውን ሆነ። 3. ታረዘ፡ ልብስ አጣ። 4. (ዘይ.) አጣ፡ ደኸየ።

አራቆተ ግ 1. ልብሱን፡ ንብረትን፡… ገፈፈ፡ መለመላ አስቀረ። 2. ልብስ ነሳ፡ ከለከለ። 3. ባዶ አስቀረ። 4. (ዘይ.) አደኸየ።

ራበ ግ 1. ምግብ አሰኘ፡ አስፈለገ። 2. ከመቸገር ወይም ለብዙ ጊዜ ምግብ ከማጣት የተነሳ የሚመጣ ስቃይ ያዘ፡ አጋጠመ።

ረሃብ (ራብ) ስ 1. የምግብ ማሰኘት፡ ማስፈለግ። 2. ችጋር፡ የምግብ መታጣት። 3. ከምግብ እጦት ወይም ማነስ የተነሳ የሚመጣና ብዙ ሰውን ለሞት የሚዳርግ ስቃይ ወይም ጠኔ።

ረሃብ ለቀቀበት በጣም ተራበ።

ረሃብ ገባ በድርቅ ወይም በሌላ ምክንያት የሚበላ እህል ጠፋ።

የረሃብ አለንጋ ጠኔ፡ ሃይለኛ ረሃብ።

የረሃብ አድማ ስ ምግብ መብላት በማቆም የሚደረግ፡ የሚቀርብ፡ የሚገለፅ ተቃውሞ (ለሚቀርበው ጥያቄ ተጠያቂው አወንታዊ ምላሽ እንዲሰጥ ለመገፋፋት)።

ተራበ ግ የሚበላው አጣ፡ በረሃብ ተጠቃ።

ራብእ ስ እንደ "**ሃ**"፡ "**ላ**"፡ "**ማ**"፡… ያሉ በሳልስና በሃምስ መካከል የሚገኙ አራተኛዎቹ የፊደላት ዘሮች መጠሪያ ወይም የድምፅ ምልክት።

ራት (እራት) ስ ምሽት(ማታ) ላይ የሚበላ የእለት ምግብ።

የራት ልብስ ስ በእራት ግብዣ ላይ ብቻ የሚለበስ የወንድ ወይም የሴት የክት ልብስ።

የራት ግብዣ ስ ማታ ላይ የሚደረግ የመብልና የመጠጥ ድግስ።

ራቻ ስ መከር ከመድረሱ በፊት ቀደም ብሎ በመድረስ ለችግር የሚውል ሰብል።

ራእይ ስ በእንቅልፍ ወይም በተመስጦ ጊዜ የሚታይ ህሊናዊ ትርኢት፡ ህልም።

ራኬት ስ የጠረጴዛ ኳስን፡ የሜዳ ቴኒስ ኳስን፡… መለጊያ ወይም መጫወቻ መሳሪያ።



ራኬት

ራዎት ስ ርኩት፡ ኮዳ፡ የውሃ መያዣ።

ራዛ ስ አንበጣ በል የሆነ ነጭ አሞራ።

ራደ ግ ፈራ፡ ተንቀጠቀጠ፡ ተብረከረከ፡ ተርበደበደ።

ርደት ስ መንቀጥቀጥ፡ መፍራት፡ መብረክረክ፡ መርበድበድ።

አራደ ግ አስፈራ፡ አንቀጠቀጠ፡ አብረከረከ።

ራዲያተር ስ የመኪና ሞተርን ግለት ለማቀዝቀዝ የሚረዳ ውሃ በውስጡ የሚይዝ የውሃ ጋን።

ራዳር ስ ተንቀሳቃሽ ነገሮች በተወሰነ የአየር ክልል ውስጥ መኖራቸውን ወይም መጓዛቸውን የሚያሳይ መሳሪያ።

ራድዮን "ራዲዮ"ን ተመ.

ራጂ ስ ክብ ነገርን፣ ጎማን ከመሃሉ የሚያያይዝ ቀጫጭን ሽቦ።



ራጅ በኤሌክትሪክ ሃይል በሚመነጭና ለአይን በማይታይ ሃይለኛ ጨረር አማካይነት የሚቀረፅ ውስጣዊ የሰውነት ክፍል ምስል፣ ኤክስሬይም ይባላል።

ራጨት "ረጨ" ስር ተመ.

ራፖር ስ ማመልከቻ።

ሬ የ"ረ" ፊደል ሃምስ ዘር።

ሬሳ ስ 1. ነፍስ የተለየው፣ የሞተ፣ በድን የሆነ አካል። 2. (ዘይ.፣ስድብ) ሙትቻ፣ አቅመቢስ።

[የ] ሬሳ ሳጥን ስ የሞተ ሰው አስከሬን እንዲቀበርበት የተዘጋጀ ሳጥን።

ሬስቶራንት ስ እየተከፈለ የሚበላበት ምግብ ቤት።

ሬብ ስ የአይነ ምድር መውጫ።

ሬባም ቅ (ስድብ) ቆሻሻ፣ ዝርክርክ፣ ፈሪ።

ሬት(እሬት) ስ ጠፍጣፋ፣ ረዘምና ሾጣጣ ያለ ቅርፅ ያለውና ወፍራም ቅጠሉን ሲፈነክቱት በሰማያዊ የሆነ መራራ ፈሳሽ የሚወጣው የእፅዋት አይነት።

ሬት ሬት አለ 1. መረረ። 2. (ዘይ.) አስጠላ፣ በጣም ሰለቸ። *ንግግሩ ሬት ሬት አለኝ።*

ሬንሳ (እሬንሳ) ስ በገጠር አካባቢ ለሃገረሰብ መድሃኒት የሚከፈል ገንዘብ።

ሬንጅ ስ ከነዳጅ ዘይት ድፍድፍ የሚገኝና ለአስፋልት ስራ የሚያገለግል ጥቁር መጣበቂያ፣ ከትራሚ።

ሬኮማንዴ ስ 1. የአደራ ደብዳቤ። 2. ህጋዊ ደብዳቤ የደረሰው ሰው ለመቀበሉ ማረጋገጫ የሚፈርምበት መዝገብ።

ሬዲዮ(ራድዮ) ስ ከአንድ የተወሰነ አካባቢ የሚተላለፈውን የድምፅ መልእክት እየጠለፈ በሚፈለገው ሁኔታ አጉልቶ የሚያሰማና በባትሪ ወይም በኤሌክትሪክ ሃይል የሚሰራ መሳሪያ።

ሬድዮ አስተላለፈ በሬዲዮ አማካኝነት መልእክትን ነገረ፣ ለሌላ እንዲደርስ አደረገ።

ሬድዮ ከፈተ በሬድዮ የሚተላለፈውን ፕሮግራም ለማዳመጥ እንዲቻል ተዘግቶ የነበረውን ሬድዮ፣ መክፈቻውን በመጠቀም እንዲሰራና ፕሮግራም እንዲያስተላልፍ አደረገ፣ አስጀመረ።

ሬድዮ ዘጋ ሬድዮኑን ዝም እንዲል፣ እንዲያቆም አደረገ።

ሬድዮ ጣቢያ ስ በሬድዮ አማካኝነት የሚተላለፉ መልእክቶች የሚሰራጩበት ስፍራ ወይም መስሪያ ቤት።

ሬጅስትራር ስ 1. በአብዛኛው በዩኒቨርሲቲ፣ በፍርድ ቤት፣ በሆስፒታል፣... ህጋዊ መረጃዎች ወይም ሰነዶች የሚቀመጡበትና ምዝገባ ባለ ጉዳይ ምዝገባ የሚደረግበት ቦታ። 2. ከላይ በተጠቀሱት ቦታዎችና የስራ አይነቶች በሃላፊነት የሚሰራ ሹም።

ር የ"ረ" ፊደል ሳድስ ዘር።

ርህሩህ "ራራ" ስር ተመ.

ርህራሄ ዝ.ክ.

ርሚጦ[ሽ] "ረመጠ" ስር ተመ.

ርምስምስ አለ "*ረመሰመሰ" ስር ተመ.

ርምድ "*ረመደ" ስር ተመ.

ርምጃ ዝ.ክ.

ርምጥምጥ "ረመጠ" ስር ተመ.

ርስት ስ 1. ቤተዘመድ የሆነ እያረሰ የሚጠቀምበትና ለተወላጅ በውርስ የሚተላለፍ መሬት፣ አፅመ ርስትም ይባላል። 2. የግል ወይም የራስ ይዞታ የሆነ ቦታ፣ መሬት።

ርስተኛ ስ በተወላጅነት ርስት አግኝቶ በመጠቀም ላይ ያለ ሰው፣ የርስት ባለቤት።

ርስተ ጉልት ስ በርስትነት ከንጉስ ይሰጥ የነበረ መሬት፣ ጉልት።

ርቀት^{1} "ራቀ" ስር ተመ.

ርቅት^{2} "ረቀቀ" ስር ተመ.

ርቢ "ረባ" ስር ተመ.

ርባታ ዝ.ክ.

ርባና ዝ.ክ.

ርባን ዝ.ክ.

ርትእ ስ ትክክለኛነት፣ ቀጥተኝነት። *ፍትህና ርትእ።*

ርቱእ ቅ 1. ቀጥተኛ። 2. ግልፅ የሆነ፣ የተብራራ። *አገላለፁ ርቱእ ነው።*

ርቱእ ተሳቢ ስ (ሰዋ.) በአረፍተ ነገር ውስጥ የተሻጋሪ ግሱ ድርጊት ተቀባይ የሆነው ቃል መጠሪያ (ለምሳሌ "ካሳ ብርቱካን በላ" በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ ' ብርቱካን' ርቱእ ተሳቢ ነው፣ ቀጥተኛ ተሳቢም ይባላል)።

ኢ-ርቱእ ተሳቢ ስ (ሰዋ.) ቀጥተኛ ያልሆነ

ተሳቢ (ለምሳሌ "አባቴ ገንዘብ ላከልኝ" በሚለው ውስጥ "ለእኔ" የሚለውን የሚያመለክተው "-ልኝ" ኢርቱእ ተሳቢ ነው)።

ርብራብ "ረበረበ" ስር ተመ.

ርብርብ ዝ.ክ.

ርብትብት "*ረበተበተ" ስር ተመ.

ርብትብት አለ ዝ.ክ.

ርብድብድ "*ረበደበደ" ስር ተመ.

ርእስ (አርእስት) ስ 1. የአንድን ፅሁፍ ወይም መፅሃፍ ፍሬ ጉዳይ የሚያመለክት የፅሁፉ ወይም የመፅሃፉ መጠሪያ። 2. አንድ ፅሁፍ፣ ውይይት፣...የሚያተኩርበት ጉዳይ ("አርእስት" የብዙ ቁጥር ቅርፅ ቢሆንም እንደነጠላ ቅርፅ ሆኖም ያገለግላል)።

አርእስት 1. ከመፅሃፍ ገፅ ላይ ከወደላናት በኩል የሚገኝ፣ ፅሁፍ ያልሰፈረበት ክፍት ቦታ፣ የህዳግ ተቃራኒ። 2. የ"**ርእስ**"ን ፍቺ ተመ.

ርእስ ሊቃነ ጳጳሳት ስ (ቤ.ክህ.)ከሊቃነ ጳጳሳት ከፍ ያለ ማእረግ ያለው ጳጳስ።

ርእስ መምህር ስ የትምህርት ቤት ስራመሪ፣ ሃላፊ፣ ዳይሬክተርም ይባላል።

ርእስ ብሄር ስ የአንድ ሃገር ወይም መንግስት መሪ።

ርእስ አንቀፅ ስ በአንድ ጋዜጣ ወይም መፅሄት ላይ በዝግጅት ክፍሉ ወይም በዋና አዘጋጁ የሚቀርብ በአብዛኛው የወቅቱን አቢይ ጉዳይ ወይም የመፅሄቱን ልዩ ትኩረት የሚመለከት ፅሁፍ።

ርእስ አውደዓመት ስ የዘመን መለወጫ በአል፣ እንቁጣጣሽ፣ መስከረም አንድ ቀን፣ የአዲስ አመት መጀመሪያ።

ርእስ ደብር ስ (ቤ.ክህ.) ማእረጉ ከሊቀ ጠበብት በታች፣ ከቀኝ ጌታና ከግራ ጌታ በላይ የሆነ የመዘምራን አለቃ።

ርኩስ "ረከሰ" ስር ተመ.

ርኩቻ "*ረኮተ" ስር ተመ.

ርካሽ "ረከሰ" ስር ተመ.

ርካብ (እርካብ) ስ በፈረስና በበቅሎ ኮርቻ ግራና ቀኝ የሚንጠለጠል፣ ለመውጣጫ፣ እግር ለማሳረፊያ፣ ሚዛን ለመጠበቂያ የሚያገለግል የኮርቻ እቃ (ስእሉን ኮርቻ ስር ተመ.)።

ርካታ "ረካ" ስር ተመ.

ርክርክ "ረከረከ" ስር ተመ.

ርክበ ካህናት ስ ከትንሳኤ በሂላ በሃያ አምስተኛው ቀን፣ ሃዋርያት ኢየሱስን ያገኙበት እለት ነው ተብሎ የሚታወስ በአል።

ርክክብ "*ረከበ^2" ስር ተመ.

ርክፍክፍ "*ረከፈከፈ" ስር ተመ.

ርዝመት "ረዘመ" ስር ተመ.

ርዝማኔ ዝ.ክ.

ርዝራዥ ስ ተርፎ የቀረ ነገር፣ ትራፊ፣ ቅሪት።

ርደት "ራደ" ስር ተመ.

ርዳታ "ረዳ" ስር ተመ.

ርጉም "ረገመ" ስር ተመ.

ርጋታ "ረጋ" ስር ተመ.

ርጋጭ "ረገጠ" ስር ተመ.

ርጋፊ "ረገፈ" ስር ተመ.

ርጋፎ ዝ.ክ.

ርግማን "ረገመ" ስር ተመ.

ርግብ (እርግብ) ስ 1. ብዙውን ጊዜ የሰላም ምልክት ተደርጋ የምትወሰድ ከአሞራ የምታንስ ከወፍ ከፍ የምትል የአእዋፍ አይነት።(ስእሉን ወፍ ስር ተመ.) 2. (ዘይ.) የዋህ፣ ገር፣ ደግ፣ ተንኮል የሌለው።

ርግብግቢት "*ረገበ" ስር ተመ.

ርግብግብ ዝ.ክ.

ርግዶ "ረገደ" ስር ተመ.

ርግጠኛ "*ረገጠ" ስር ተመ.

ርግጥ ዝ.ክ.

ርግጫ "ረገጠ" ስር ተመ.

ርግፍ ርግፍ አለ "ረገፈ" ስር ተመ.

ርግፍ አደረገ ዝ.ክ.

ርግፍግፍ አለ ዝ.ክ.

ርጥ "ረጠጠ" ስር ተመ.

ርጥበት "ረጠበ" ስር ተመ.

ርጥብ ዝ.ክ.

ርጥጥ "ረጠጠ" ስር ተመ.

ርጭ አለ "እርጭ አለ" ን ተመ.

ሮ የ"ረ" ፊደል ሳብእ ዘር።

ሮማን ስ መጠኑ ብርቱካን የሚያክል፣ ውስጡ ቀያይና ትንንሽ የሆኑ ጠንካራ የዘር ፍሬዎች በብዛት ያሉትና ጣፋጭ የሆነ ፍሬ፣ ተክሉም **ሮማን** ይባላል።

ሮሮ (እሮሮ) ስ 1. ሃዘን፣ ዋይታ። 2. ስሞታ፣ ብሶት።

ሮስተር ስ የተማሪዎች የትምህርት ውጤት የሚሰፍርበት መዝገብ።

ሮቃ ስ ፍሬውን ሲበሉት የሚኮመጥጥ የብርብራ አይነት ዛፍ፣ ሆመርም ይባላል፣ ፍሬውም ሮቃ (ሆመር) ይባላል።

ሮቄ ስ ማጥ፥ ረግረግ፥ አረንቋ።

ሮብ "ረቡእ" ን ተመ.

ሮንዴላ ስ የታሰረ ብሎን በንቅናቄ እንዳይፈታ አፍና የሚይዝ፥ መሃሉ ክፍት የሆነ ክብና ጠፍጣፋ ብረት ወይም ጎማ።

ሮጠ ግ 1. ቶሎ ቶሎ ተራመደ፥ በፍጥነት ሄደ፥ ሸመጠጠ። 2. ቸኰለ፥ ተጣደፈ። *ለጠብ ለምን ትሮጣለህ።*

ሩጫ ስ 1. የጥድፊያ፥ የችኰላ፥ የፍጥነት እርምጃ። 2. ችኰላ፥ ጥድፊያ። 3. በበለጠ ፍጥነት በመሮጥ ሌላውን ለመቅደም የሚደረግ ስፖርታዊ ውድድር፥ እሽቅድድም።

ሯጭ ቅ 1. ፈጣን። ስ 2. በሩጫ ውድድር የሚካፈል፥ የሚወዳደር ስፖርተኛ።

ተሯሯጠ ግ 1. ሌላውን ለመቅደም፥ ለመከተል፥ ለማሳደድ ወይም ተከታትሎ ለመድረስ ሮጠ። 2. ወዲያ ወዲህ አለ፥ ተዋከበ (ጉዳይ ለመፈፀም፥ አንድ ነገር ለማግኘት፥...)።

አሯሯጠ ግ 1. አሳደደ፥ አባረረ፥ ለመያዝ፥ ለመምታት፥... ቢል ተከትሎ ሮጠ። 2. አጣደፈ። 3. አዳከመ፥ አለፋ።

አሮጠ ግ 1. እንዲሮጥ አደረገ፥ አጣደፈ። 2. አለፋ፥ አደከመ፥ ወዲያ ወዲህ አሰኘ።

ሯ የ "ረ" ፊደል ፍንፅቅ ዘር።

ሯጭ "ሮጠ" ስር ተመ.

ሰ

ሰ ከ "ረ" ፊደል ዘር ቀጥሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል (ግእዙ ሠሃ)::

ሰሃ (ሰሃ) ስ እንከን፥ ሳካ፥ ሳንካ::

ሰሃን "ሳህን" ን ተመ.

ሰለለ^1 ግ 1. ቀጠነ፥ መነመነ:: 2.ቀጠነ(ለድምፅ)::

ሰላላ ቅ 1. ቀጭን፥ የመነመነ:: 2. ቀጭን(ለድምፅ):: *ድምፀ ሰላላ*::

ሰላላ መላላ ቅ ትክክል ያልሆነ፥ ቀጭንና ወፍራም ሆኖ የተፈተለ(ፈትል)::

አሰለለ ግ አቀጠነ፥ አመነመነ::

ሰለለ^2 ግ 1. በማየት፥ በመስማት ወይም በሌላ ዘዴ የሌላውን ወገን ምንነት፥ ሁኔታ፥... በሚመለከት ምስጢራዊ መረጃ አጠናቀረ፥ ሰበሰበ:: 2. አየ፥ ተመለከተ፥ ቃኘ::

ሰለል ብሎ ገባ ሰተት ብሎ ሳይታወቅ፥ ሳይሰማ ገባ::

ሰላይ ስ ምስጢራዊ መረጃ የሚያጠናቅርና የሚሰበስብ ሰው::

ስለላ ስ የመሰለል ተግባር::

[የ]ስለላ ድርጅት ስ የስለላ ስራን የሚያካሂድ ድርጅት::

ተሰለለ ግ አንድን ሰው፥ ሃገር፥... በተመለከተ ምስጢራዊ መረጃ ተሰበሰበ፥ የስለላ ተግባር ተካሄደበት::

ተሳለለ ግ የማጠያየቅ፥ የማፈላለግ ስራ ሰራ፥ አየ፥ ቃኘ:: *ልጅ ጠፍቶብኛልና እስኪ በአካባቢው ተሳለሉልኝ*::

አሰለለ ግ 1. ሰላይ ምስጢራዊ መረጃ እንዲያገኝ አደረገ፥ ሁኔታን አመቻቸ:: 2. በሌላው ላይ ስለላ እንዲካሄድ አደረገ::

አሳሰለ ግ አጠያየቀ፥ አፈላለገ፥ አየ፥ ቃኘ::

ሰለመ^1 ግ የእስልምና ሃይማኖትን ተቀበለ፥ እስላም ሆነ::

ሙስሊም ስ እስላም::

እስላም ስ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ፤ሙስሊም::

እስልምና ስ በነቢዩ መሃመድ የተመሰረተና አላህን ብቸኛ አምላክ፥ ነቢዩ መሃመድን የአላህ መልእክተኛ ወይም ነቢይ አድርጎ የሚቀበል ሃይማኖት::

ሰለመ^2 ግ 1. ጨለመ:: 2. ደከመ፥ ዛለ (አይን፥ ሰውነት፥ ...)::

ስልም አለ ግ 1. ጭልም አለ:: 2. ዛል፥ ድክም አለ::

ስልምልም ቅ ዝልፍልፍ ወይም ድክም ያለ::

ስልምልም አለ ግ 1.ዝልፍልፍ ወይም ድክም አለ:: 2. አይኑ በድካም መልክ ክፍት ክድን አለ::

ስልምልም አደረገ ግ አዝለፈለፈ፥ አደካከመ፤ አይኑን ክፍት ክድን አደረገ::

ተስለመለመ ግ 1. ተዝለፈለፈ፥ ድክምክም አለ:: 2. በድካም መልክ ክፍት ክድን አለ(አይኑ)::

አስለመለመ ግ 1. አዝለፈለፈ፥ አደከመ:: 2. በድካም መልክ ክፍት ክድን አደረገ(አይኑን)::

***ሰለመ**

ሰላም ስ 1. ረብሻ፥ ሁከት፥ ጦርነት የሌለበት፥ የተረጋጋ ሁኔታ:: 2. ደህንነት፥ ጤንነት፥ የአእምሮ እረፍት:: 3. በቁም ዜማና በማህሌት መጨረሻ ላይ የሚባል ዜማ::

ሰላም አለ ሰላምታ ሰጠ::

ሰላም ወዳድ ሰላምን የሚፈልግ፥ ለሰላም የቆመ::

በሰላም ተው.ግ. 1. በደህና፥ አደጋ በሌለበት ሁኔታ:: *በሰላም ይመለሱ*:: 2. ጠብ፥ ረብሻ፥ ግጭት በሌለበት ሁኔታ:: *በሰላም አብረን እንኖራለን*:: 3. በተረጋጋ መንፈስ:: *ስራዬን በሰላም መስራት እፈልጋለሁ*::

በሰላም(በሰላማዊ) መንገድ በመግባባት መልክ፥ ቅራኔን በውይይት በመፍታት፥ ያለ መሳሪያ ትግል::

የሰላም ልኡካን ስ ሰላምን ለማስፈን፥ እርቅን ለማውረድ፥... የተላኩ መልእክተኞች::

የሰላም ውል ስ በጠብ ወይም በጦርነት ያሉ መፈላለግ ውል::

የሰላም ጉባኤ ስ በሃገሮችና በህዝቦች መካከል ሰላም እንዲሰፍን፥ ወንድማማችነትና የጋራ ትብብር እንዲዳብር ለማድረግ የሚደረግ ስብሰባ::

ሰላማዊ ቅ 1. በወታደራዊ እንቅስቃሴ ወይም በጦርነት ላይ ተሳትፎ የሌለው:: 2. በወንጀል ወይም በሽብር ፈጠራ ተሳትፎ የሌለው::

ሰላማዊ ሰልፍ ስ ፖለቲካን ኢኮኖሚንና ማህበራዊ ጉዳይን አስመልክቶ ደስታን ቅሬታን ለመግለፅ፥ ጥያቄን ለማቅረብ፥መፈክሮችን በመያዝና በአንደበትም በማሰማት በርካታ ሰው በሚገኝበት አካባቢና በአደባባይ በይፋ የሚደረግ ሰልፍ ወይም ስብሰባ፥ ትእይንተ ህዝብ::

ሰላምታ ስ ሰዎች ሲገናኙ እጅ በመጨባበጥ፣ ከአንገት ጎንበስ በማለትና እንደምነህ፣ እንደምነሽ በመባባል ወዘተ. ወይም በመልእክተኛ፣ በደብዳቤ የሚለዋወጡት የመልካም ምኞት መግለጫና የጤንነት ጥያቄ።

ሰላምታ ሰጠ ለሰላምታ እጁን ዘረጋ፣ አጎነበሰ ፣ እጅ ነሳ።

ሰላምታ ነፈገ ሰላምታ መስጠት ተወ ወይም ከለከለ።

ሰላምተኛ ቅ ትሁት፣ ትህትና ያለው፣ ሰላምታ ሳይሰጥ የማያልፍ።

ተሳለመ ግ ቤተክርስቲያንን፣ መስቀልን፣ ቅዱሳት መፃህፍትን፣ የቄስ እጅን፣ ...በመሳምና እጅ በመንሳት ለእግዚአብሄር ያለውን አምልኮት ወይም ክብርና ምስጋና ገለፀ።

መሳለሚያ ስ በቤተክርስቲያን አንፃር ወይም ትይዩ ባለ መንገድ ላይ መንገደኛ የሚሳለምበት የእጅ መንሻ ወይም የመሳለሚያ ምልክት (ለምሳሌ የተከመረ ድንጋይ) ያለበት ቦታ።

ተሳላሚ ስ ቤተክርስቲያንን ለመሳለም ወይም ለማስቀደስ የሚሄድ ሰው።

አሳለመ ግ 1.ቄሱ እጁን ወይም መስቀልን፣ ዲያቆኑ ቅዱሳት መፃህፍትን በማቅረብ ምእመናን እንዲሳለሙ አደረገ። 2. (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) አስከሬን ወደ መቃብር ከመውረዱ በፊት የቤተክርስቲያንን ደጃፍ ሶስት ጊዜ እጅ እንዲነሳ አደረገ፣ አሰገደ(አስከሬኑን ለ3 ጊዜ ዝቅ ከፍ እያደረጉ በማስገድ)።

ሰለሰ ግ 1. ለሶስተኛ ጊዜ አደረገ ወይም ደገመ። 2. ውሃ ጨመረ (በወጥ፣ በጠላ፣... ውስጥ)።

ሰልስት(ሳልስት) ስ 1. አንድ ቀን አልፎ ያለው ሶስተኛው ቀን። 2. ሙት የተቀበረበት ወይም አፈር የቀመሰበት ሶስተኛ ቀን።

ሰልስትና(ሳልስትና) ከትናንት ወዲያ።

ሳልሳይ(ሳልሳዊ) ቅ ሶስተኛ። *ሳልሳይ ዮሃንስ።*

ሳልስ ስ እንደ "ሂ"፣ "ሊ"፣ "ሚ"፣... ያሉ በካእብና በራብእ መካከል የሚገኙ ሶስተኛዎቹ የፊደላት ዘሮች መጠሪያ ወይም የድምፅ ምልክት።

ስሉስ ስ 1. በገበጣ ጨዋታ፣ ሙግ ሊወጋበት የሚችል ሶስት ጠጠር ያለበት ቤት። 2. የሶስት ቡድን፣ ሶስት በአንድነት። *በስሉስ ቆኖ በሺ ሰርግኝ ልማ በስሉስ ገፉ በስሉስ።*

ስሉሴ ስ በብር ወይም በወርቅ ወይም በነሃስ መደብ ላይ በ3 በ3 ረድፍ ተንጠልጥሎ (፩፩፩) ሆኖ የሚሰራና በበቅሉ አንገት ላይ የሚደረግ ጌጥ።

ሰላሴ ስ 1. (ክር.) የእግዚአብሄር በአካል፣ በስም፣ በግብር የሶስትነቱ መግለጫ ስም። 2.የታቦት ስም። 3. ስድስት ቤት ያለው የቅኔ አይነት።

ተሰለሰ ግ ሶስት ጊዜ ተደረገ፣...።

አሰለሰ ግ 1. ሶስት ጊዜ አደረገ ወይም ሰራ። 2.በየሶስተኛው ቀን መጣ ወይም ሄደ።

አያሰልስም አያቋርጥም፣ ሁልጊዜ ይመጣል ወይም ይሄዳል፣ ወይም አንድን ነገር ሁልቀን ያደርጋል።

ሰለሰለ ግ 1. ቀጠነ፣ መነመነ፣ ሰለለ። 2. ሰነጠቀ፣ ሸነሸነ (ስጤንን፣ ግራምጣን፣...)።

ሰልሳላ ቅ ቀጭን፣ መንማና፣ ሰላላ።

አሰለሰለ ግ አቀጠነ፣ አመነመነ፣ አሰለለ።

ሰለቀ ግ 1. ፈጨ፣ ደቆሰ፣ አለዘበ፣ አላመ፣ አደቀቀ። 2. አመመ፣ አደከመ። *በሽታው ሰለቀው።* 3. አዘረጠ፣ መታ (በዱላ፣ በክርን)።

መሰለቂያ(መሰለቂት) ስ ማላሚያ ወፍጮ (የመገርደፊያ ተቃራኒ)።

ስልቅ ቅ የተፈጨ፣ የላመ፣ የደቀቀ (እህል)።

ተሰለቀ ግ በጣም ደቆ ተፈጨ፣ ላመ።

***ሰለቀ**

ስላቅ ስ ፌዝ፣ ለግጥ፣ ቀልድ።

ተሳለቀ ግ አፌዘ፣ አላገጠ፣ ቀለደ፣ አሾፈ።

ተሳልቆ ስ ስላቅ።

ሰለቀጠ ግ ሳያኝክ ወይም ሳያላምጥ ዋጠ።

ሰለበ ግ 1. የወንድን አባለዘር ቆረጠ። 2. በምትሃት፣ በዘዴ፣ በአስማት፣ የሰውን ገንዘብ ወሰደ። 3. አደከመ፣ አዛለ። *በሽታው ልቡን ሰለበው።* 4. ዘጋ (ድምፁን)።

ሰለባ ስ 1. የግዳይ፣ የድል ምልክት፣ ምርኮ። 2. በዝርፊያ ወይም በቅሚያ የተሰበሰበ እቃ ወይም ንብረት። 3. በሌላ ሰው ድርጊት ወይም በተለያዩ አደጋዎች ምክንያት መከራ፣ ችግር፣ ጉዳት የደረሰበት ሰው፣ አገር፣...። *የጦርነቱ ሰለባዎች ብዙ ናቸው።*

ሰላቢ ስ 1. በምትሃት፣ ባስማት ወይም ሳይታወቅበት የሰውን ገንዘብ የሚወስድ። 2.(ስድብ) ሾካካ፣ ቀትረ ቀላል።

ስልብ ቅ አባለዘሩ የተቆረጠ (ሰው)።

ተሰለበ ግ 1. አባለዘሩ ተቆረጠ። 2. ተፋጠነ፣ ተቀላጠፈ፣ በፍጥነት ተከናወነ፣ ተካሄደ። *እገሌ መንገድ፣ ስራ፣...ይሰለብለታል።* 3. ጠፋ፣ ተሰወረ።

ሰለተ¹ ግ የሳር ቤትን ሲሰራ ሰንበሌጡን ወይም

ስሩን፣...አናቱን ወደታች ስሩን ወደላይ አድርጎ ከደነ።

ሰለታ ስ የሰንበሌጡ ወይም የሳሩ አናት ወደታች ተዘቅዝቆ፤ ቂጡ ወደላይ ተደርጎ የሚሰራ የሳር ቤት አከዳደን አይነት፤ የክፍክፍ የቤት አከዳደን ተቃራኒ።

ሰለተ^2 ግ 1. ከሳ፤ ቀጠነ፤ መነመነ። 2. ፍሬ አልባ ሆነ፣ ከሰመ፣ ጠወለገ፣ ደረቀ።

ሰለታ "ሰለተ^1" ስር ተመ.

ሰለቸ ግ 1. ታከተ፣ ደከመ። 2. ተመረረ፣ ተንገፈገፈ፤ ጠላ (አንድን ነገር ደጋግሞ በመስራት፣ በማየት፤ በመስማት፣...)። 3. አስጠላ፤ አስቀየመ (ተደጋግሞ በመሰራቱ፣ በመታየቱ፤ በመሰማቱ)።

ስልቹ ቅ ቶሎ የሚጠላ፣ የሚሰለች፣ የሚታክት።

ተሰለቸ ግ በመደጋገሙ ተጠላ።

ተሰላቸ ግ ሰለቸ፤ ጠላ፤ ታከተ።

አሰለቸ ግ 1. አደከመ፣ አታከተ፤ አንገፈገፈ፤ አስጠላ (በመብዛት፤ በመደጋገም)። 2. ደጋግሞ ጠየቀ ወይም ለመነ፣ ጨቀጨቀ።

አሰልቺ ቅ 1. በጣም አድካሚ የሆነ፤ የሚያሰለች። 2. ጨቅጫቃ፤ በልመና፣ በጥያቄ የሚያሰለች።

*ሰለከለከ

ሰለክላካ (ስልክልክ) ቅ እንደ እባብ ሹልክልክ እያለ የሚሄድ።

ተሰለከለከ ግ ተሸሎከሎከ።

*ሰለከከ

ስልክክ ቅ አፍንጫው ቀጠንና ረዘም ብሎ የወረደ፤ መልከ ቀና፣ ቆንጆ (ሰው)።

ስልክክ ያለ ቀጥ ብሎ የወጣና የሚያምር (አፍንጫ፣ መልክ)።

ሰለክላካ "*ሰለከለከ" ስር ተመ.

ሰለጀጀ ግ ደከመ፣ ፈዘዘ፣ ነሆለለ።

ስልጃጃ ቅ ፈዛዛ፣ ነሁላላ።

ተንሰለጀጀ ግ ደከመ፤ ፈዘዘ።

አንሰለጀጀ ግ አደከመ፤ አፈዘዘ።

ሰለጠ ግ ቀና ሆነ፤ ተከወነ፣ ቀለጠፈ።

አሰለጠ ግ ቶሎ ቶሎ አከናወነ፣ አፍጥኖ ጨረሰ።

ሰለጠነ ግ 1. አደገ፤ ተሻሻለ፤ ዘመናዊ ሆነ፤ ከፍ ወዳለ የእውቀት ደረጃ ደረሰ፣ ከኋላ ቀርነት ራቀ (ሃገር፤ ህዝብ)። 2. አንድን ነገር ማድረግ ወይም መስራት አወቀ፤ ለመደ። 3. ተሻሻለ፤ ንቁ ሆነ፤ ቀለጠፈ። 4. አንድን ሙያ ተማረ፤ ተካነ፣ ትምህርት አገኘ። *በህክምና ትምህርት ሰለጠነ።* 5. ምቹ ሁኔታ አገኘ፤ አየለ። *ገደል ባለበት ሃገር ዝንጀሮ ይሰለጥናል።*

ስልጠና ስ አንድን ተግባር ወይም ድርጊት በተሳካ ሁኔታ ለማከናወን የሚያስችል እውቀት፣ ተግባራዊ ትምህርት፣ ልምምድ።

ስልጡን ቅ 1. ንቁ፣ ቀልጣፋ፤ ጨዋ፤ ትሁት፤ ስርአት ያለው። 2. ስልጠና ያገኘ፣ የሰለጠነ።

ስልጣኔ ስ እድገት፤ ዘመናዊነት፣ ከፍተኛ የእውቀት ወይም የመሻሻል ደረጃ።

ስልጣን ስ 1. አንድን ነገር ለማድረግ፣ ለመስራት ወይም ለማሰራት የሚያስችል መብት። 2.የመንግስት አስተዳደርን ወይም አመራርን በበላይነት ለማካሄድ የሚያስችል ሃይል። 3. ሹመት፣ ሃላፊነት። 4 (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) የድቁና ወይም የቅስና፣... ማእረግ፤ ክህነት።

ስልጣኑን አሳየ የተሰጠውን ሃላፊነት ተጠቅሞ እርምጃ ወሰደ።

ስልጣን ያዘ ስልጣን ጨበጠ፣ ሹመት አገኘ (አብዛኛውን ጊዜ የመንግሥትን)።

ባለስልጣን ስ እንድን ነገር ለማድረግ፣ ለመስራት ወይም ለማሰራት አመራርን ለመስጠት ፡ለመወሰን የሚያስችል መብት ያለው ግለሰብ ወይም ድርጅት።

ከስልጣን በላይ ስልጣኑ ከሚፈቅድለት፣ ወይም ከችሎታው ክልል ውጭ።

የስልጣን ሽሚያ ስ ስልጣንን ለመያዝ ወይም ለመጨበጥ የሚደረግ ውድድር፤ ሽኩቻ።

የስልጣን ጥመኛ ቅ ከፍተኛ የሆነ የስልጣን ጉጉት ያለው።

አሰለጠነ ግ 1. አሳደገ፣ አሻሻለ፣ ዘመናዊ አደረገ፣ ከፍ ወዳለ የእውቀት ደረጃ አደረሰ። 2.አንድን ነገር ማድረግ ወይም መስራት አስለመደ፤ ሙያን አስተማረ፣ አሳወቀ። 3 ንቁ፣ ቀልጣፋ አደረገ።

ማሰልጠኛ ስ አንድ አይነት የሙያ ትምህርት የሚሰጥበት ተቋም።

አሰልጣኝ ቅ አንድን ሙያ የሚያስተምር።

ሰለፈ ግ 1. ሰደረ፣ ደረደረ። 2. አንድ ነገር ለማድረግ ተዘጋጀ፣ ቸኮለ፣ አቆበቆበ፣ በጣም ጓጓ። 3. ለጦርነት፤ ለውጊያ ተዘጋጀ።

ሰልፍ ስ 1. ረድፍን፤ መስመርን፣ ተርታን የያዘና ስነ ስርአትን የተከተለ የእግር ጉዞ። 2 . ረድፍን፣ መስመርን፣ ተርታን ይዞ ስነ ስርአት ባለው ሁኔታ የቆመ የሰዎች ስብስብ። 3. ተራ ወይም ቅደም ተከተል ያለው ወይም ረድፍ የያዘ አቋቋም፤ አቀማመጥ።

ሰልፈኛ ስ ረድፍን፣ መስመርን፣ ተርታን ይዞና ስነስርአትን ተከትሎ በመጓዝ ወይም በመቆም ሰልፍ ውስጥ የሚሳተፍ ሰው፣ ወይም የሚሳተፉ ሰዎች በጠቅላላ።

ተሰለፈ ግ 1. በተርታ፥ በረድፍ፣ በመስመር ገባ፥ ተደረደረ፥ ተሰደረ፥ ተራ ያዘ። 2. በሰላማዊ ሰልፍ ወይም በሌላ ሰልፍ ተሳተፈ።

ተሰላፊ ስ ሰልፈኛ።

አሰለፈ ግ በሰልፍ፣ በረድፍ፣ በመስመር እንዲሆን አደረገ።

አሰላፊ ስ የሰልፍ አስተባባሪ።

አሰላለፍ ስ በስፖርት ግጠሚያዎች የተጨዋቾች የቦታ አያያዝ፥ምደባ።

ሰሊጥ ስ የሚበል ዘይት የሚወጣውን ፍሬ የሚያፈራ ሰብል፣ ፍሬውም ሰሊጥ ይባላል።

ሰላ^{1} ግ 1. ስለታም ሆነ፣ ተባ፥ ሾለ። 2.(ዘይ.) ጎበዝ ሆነ፥ ቀለጠፈ። 3. ሾለከ። *ውሃ በቀዳዳ ሰልቶ ይወርዳል።* 4. (አባያ የነበረው በሬ) ተስተካከለ፣ ተገራ።

ስል ቅ 1. ስለት ያለው፥ በቀላሉ መቁረጥ የሚችል። 2. (ዘይ.) ብልህ፣ ቀልጣፋ፥ ጎበዝ የሆነ።

ሰላ^{2} ግ በጀ፣ አማረ፣ ቀና፣ ሰመረ፥ ተሳካ።

ሰላ በልልኝ ገር፥ ቀና ሁንልኝ።

አይሰላለትም አይሳካለትም።

ተሳሳ ግ 1. ተቀናበረ፥ ተሳካ፣ ተከናወነ። 2. ተስማማ፣ ገጠመ። *ምፈርና እርፉ ተሳሳለት።*

አሳሳ ግ አስማማ። *ምፈርና እርፉ ሳሳለት ማረስ ይችላል።*

ሰላ^{3} ግ ማረሻ ቀና ብሎ ወደ ሞፈሩ በመጠጋቱ ወይም ዶማ ጋደም ብሎ ወደ እጀታው በመጠጋቱ ጠለቅ አድርጎ የማያርስ ወይም የማይቆፍር ሆነ።

ስል ቅ የሰላ (ማረሻ፥ ዶማ)።

አሰላ ግ በጣም ጋደም እንዲል፥ ወደ እጀታው ወይም ወደ ሞፈሩ እንዲጠጋ አድርጎ አበጀ (ዶማን ወይም ማረሻን)።

*ሰላ

ስሌት ስ የመደመር፥ የመቀነስ፣ የማብዛትና የማካፈል ስራ።

ተሳሳ ግ ተሳሰበ፥ ተቆጣጠረ።

አሰላ ግ ሂሳቡን አሰበ (ደመረ፥ ቀነሰ፥ አበዛ፣ አካፈለ)።

ሰላላ "ሰለለ^{1}" ስር ተመ.

ሰላማዊ "*ሰለመ" ስር ተመ.

ሰላም ዝ.ከ.

ሰላምተኛ ዝ.ከ.

ሰላምታ ዝ.ከ.

ሰላሱት ስ ክክ።

ሰላሳ ስ 1. በሃያ ዘጠኝና በሰላሳ አንድ መካከል ያለ ቁጥር መጠሪያ። በአሃዝ ሲፃፍ ፴፥30 ነው። ቅ 2. ብዛቱ ሶስት አስሮችን የሚያክል የቁጥር መጠን። *ሰላሳ መኪኖች።*

ሰላቢ "ሰለበ" ስር ተመ.

ሰላት(ሶላት) ስ የእስልምና ሃይማኖት ፀሎትና ስግደት።

ሰላቶ "ሶላቶ" ን ተመ.

ሰላይ "ሰለለ^{2}" ስር ተመ.

ሰላጣ ስ ቅጠሉ ሳይቀቀል ለምግብነት የሚያገለግል የተክል አይነት።(ስእሉን ቅጠላቅጠል ስር ተመ.)

ሰላጤ ስ 1. ሹል ወይም ሾጣጣ የሆነ ነገር። 2. በሱሪ ወይም በሌላ ልብስ ላይ ሾጠጥ ብሎ የተሰፋ ወሸመጥ።

ሰሌን ስ 1. የዘምባባ ቅጠል። 2. ከዘምባባ ቅጠል የሚሰራ ምንጣፍ።

ሰሌን ባርኔጣ ስ ከዘምባባ ቅጠል የሚሰራ ባርኔጣ።

ሰሌዳ ስ በላዩ ለመፃፍ፣ ማስታወቂያ ለመለጠፍ ወዘተ. የሚያገለግል ዝርግና ጠፍጣፋ የሆነ እንጨት፣ ክርታስ የመሳሰለ ቀም / ልጥፍ ነገር።

ሰልሳሳ "ሰለሰለ" ስር ተመ.

ሰልስት "ሰለሰ" ስር ተመ.

ሰልስትና ዝ.ከ.

ሰልካካ "*ሰለከከ" ስር ተመ.

ሰልጃጅ "ሰለጀጀ" ስር ተመ.

ሰልፈኛ "ሰለፈ" ስር ተመ.

ሰልፍ ዝ.ከ.

ሰመለለ ግ ሹው አድርጎ ጠጣ፥ ሸመጠጠ።

ሰመመ ግ አሸለበ፣ አንቀላፋ፥ አንጎላጀ፥ ፈዘዘ።

ሰመመን ስ ሽልብታ፣ እንቅልፍ፣ የመፍዘዝ ሁኔታ።

ሰመመናም ቅ የሚደብት፣ የሚጫጫን፥ የሚያፈዝ(ሁኔታ፣ እድራጎት፥...)።

ሰመረ ግ አማረ፥ ጥሩ ሆነ፣ ተሳካ።

ስምረት ስ የማማር፥ የመሳካት ሁኔታ።

አሰመረ ግ አሳካ፥ ጥሩ አደረገ።

***ሰመረ**

መስመር ስ 1. ቀጥተኛነት ያለውና ረዘም ያለ የቀለም፣ የእርሳስ ወይም የሌላ ነገር ጭረት። 2. አቅጣጫ። *የንግዳችን መስመር በሰሜን በኩል ነው።* 3. አርእስት። *ውይይታችን መስመሩን ለቋል።* 4. ተርታ፣ መደዳ፡ ሰልፍ። 5. ፅሁፍን በቀጥታ፣ በተርታና ወጣ ገባ ሳይል ለመፃፍ እንዲያስችል በሚፃፍበት ነገር ላይ የተደረገ ምልክት። 6. ፈር፣ ስርአት። *ስራው መስመር ይዟል።* 7. መመላለሻ፣ መጓጓዣ፣ መገናኛ መንገድ። 8. ጣቢያ (የሬዲዮ)። 9. መመሪያ። *ትክክለኛ የሆነ የፖለቲካ መስመር ይከተላል።*

መስመር ለቀቀ ተሳሳተ፡ ትክክል ባልሆነ መንገድ ሄደ።

መስመር ዘረጋ እንደ የኤሌክትሪክ፣ የቴሌፎን፣ የውሃ፣ የፍሳሽና የትራንስፖርት ያለ የአገልግሎት አውታር ዘረጋ፣ አበጀ፣ አዘጋጀ፣ አቋቋመ።

ከመስመር ወጣ ከደንብ፣ ከስነ ስርአት ውጭ ሆነ።

ከመስመር ውጪ የእግር፣ የመረብ፣ የቅርጫት ኳስ በመሳሰሉት ጨዋታዎች ከተዘጋጀውና በምልክት ከተከለለው ወይም ከተፈቀደው የሜዳ ክልል ውስጥ የኳስ መውጣት።

የመስመር ዳኛ ስ በኳስ ጨዋታ ጊዜ የመሃል ዳኛውን ለመርዳት በኳሱ ሜዳ በስተግራ ወይም በስተቀኝ ሆኖ የሚያገለግል ረዳት ዳኛ።

ተሰመረ ግ ቀጥ ያለ መስመር ተደረገ።

አሰመረ ግ ቀጥተኛ መስመር ነደፈ።

አሰመረበት አፅንኦት ሰጠው።

ማስመሪያ ስ ከእንጨት ወይም ከብረት ወይም ከፕላስቲክ ወዘተ. የሚሰራ፣ ቀጥተኛ ጎን ያለውና ቀጥ ያለ መስመር ለመስራት የሚያገለግል፣ ቀጭን፣ ረዥም የሆነና በተወሰነ የርዝመት መለኪያ (በሳንቲ ሜትር፣ በኢንች፣...) መጠን የተከፋፈለ የፅህፈት መሳሪያ(ስእሉን የፅህፈት መሳሪያ ስር ተመ.)።

ሰመሬታ ስ በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚደርስ የገብስ አይነት።

***ሰመር**

ሰመር ገባ (በትግል ውድድር ላይ) ተያዘ፣ ተሸነፈ፣ በቁጥጥር ስር ሆነ።

ሰመር ገጠመ በትግል ወይም በትንቅንቅ ጊዜ ወገብ ለወገብ አጥብቆ ተያያዘ።

ሰመሰመ ግ ቶሎ ቶሎ ጎረሰ፤ በላ።

***ሰመነመነ**

ተሰመነመነ ግ ደከመ፡ ደቀቀ፣ ቀሰለመለመ(በእንቅልፍ፣ በበሽታ፣ በድካም)።

አሰመነመነ ግ አደቀቀ፣ አደከመ።

ሰመማ ስፍራው ጥቁረትና ንጣት የተደባለቀበትና በቆላ አካባቢ የሚገኝ እንደ ሃረግ ያለ የእፅዋት አይነት።

ሰመማማ ቅ እንደ ሰመማ ፍሬ ዥንጉርጉር፣ ወይም ጠቃጠቆ መልክ ያለው (ለከብት)።

ሰመጠ(ሰጠመ) ግ ጠለቀ፣ ገባ፡ ሰረገ፡ ዘቀጠ።

ስምጥ ቅ ጥልቅ።

ስምጥ ሸለቆ ስ በመሬት መሰንጠቅና በመስረጉ ምክንያት የተፈጠረ በሰሜን ምስራቅ አፍሪቃ የሚገኝ ጥልቅና ረባዳ ሸለቆ።

ስምጥ ስምጥ አለ ግ ትምቡህ ትምቡህ አለ።

አሰመጠ (አሰጠመ) ግ 1. ወደ ውስጥ አጠለቀ፡ አገባ፡ አሰረገ (ውሃ ፡ ረግረግ፣...)። 2. አጠለቀ፡ ዘፈቀ፡ በብዛት ወጣ (ሳቡ)።

ሰመጠጠ^{1} ግ ሸመጠጠ፡ ጨለጠ፡ ጠጣ።

ሰመጠጠ^{2} ግ ከተተ፡ እስከ መጨረሻው አስገባ (ሰንጢ፡ ጩቤ፡...)።

ሰሙነ ህማማት "ሰሞን" ስር ተመ.

ሰማ^{1} ግ 1. አደመጠ። 2. ተቀበለ፣ የተነገረውን ያዘ፡ ተረዳ። *ምክር ይሰማል።*

ይሰማል በመጠኑ ያውቃል። *ላማርኛ ይሰማል።*

ሰማልኝ አስተውል፣ ታዘብ፣ ልብ አድርግ።

ሰማ በለው ስ የቃል ትርጁማን፣ አስተርጓሚ።

በሰማበለው በአስተርጓሚ። *ከፈረንጁ ጋር በሰማ በለው ተነጋገርኩ።*

ሰማ ተሰማማ በቀድሞ ጊዜ አዋጅ ለመንገር ሲፈለግ ይህን አዋጅ እድምጥ፣ ሳልሰማም ንገር ለማለት አዋጁ በሚነገርበት ቦታ ላይ በመጀመሪያ የሚባል የተሰብሳቢውና የአዋጅ ሰሙ ጥሪ ማሰሚያ ቃል።

ለይሰሙላ ለወሬ፣ ለስም ያህል፣ በትንሹ።

ሰሚ ቅ 1. አድማጭ ወይም አዳማጭ። 2. አሺባይ፣ ተቀባይ።

አልሰሜ ቅ ያልሰማ፣ ያልተረዳ፣ ለነገሩ እንግዳ የሆነ (ሰው)።

ሰሚ ስ ጭምጭምታ፣ ወሬ።

የሰሚ ሰሚ ስ ጭምጭምታ፣ የወሬ ወሬ።

ሰሜት ስ 1. በአእምሮ ወይም በአካል ላይ የሚንፀባረቅ የአንድ ነገር ተፅእኖ ውጤት። 2. ፍላጎት፣ ዝንባሌ (ለመስራት፡ ለማወቅ፣...)።

ስሜቱ ተቀሰቀሰ /ተነሳሳ አንድን ነገር ለመስራት፥ ለማግኘት፥ ለማወቅ ያለው ጉጉት ከፍ አለ።

ስሜት አይሰጠውም ደንታ የለውም፥ ግድ የለውም።

የስሜት ህዋሳት ስ ለመስማት፥ ለመቅመስ፥ ለማየት፥ ለመዳሰስና ለማሽተት የሚያገለግሉ እንደ ጆሮ፥ ምላስ፥ አይን፥ አፍንጫ የመሳሰሉ የሰውነት ክፍሎች።

ስሜታዊ ቅ በግል ፍላጎት የተመረኮዘ፥ ተጨባጭ መለኪያ የሌለው።2.ነገሮችን ሳያገናዝብ በስሜቱ ብቻ የሚመራ(ሰው)።

ስምም ቅ 1. ጥል፥ ቅዋሜ፥ ግጭት የሌለው። ስ 2. ፍቅር፥ ወዳጅ፥ ሰላም።

ስምሙ ቅ ስምም።

ስምምነት ስ 1. ፍቅር፥ ወዳጅነት፥ መግባባት። 2. ውል። 3. በመወያየት ወይም በመነጋገር የሚደረስበት ይሁንታ።

ስሞታ ስ እገሌ እንዲህ ሰራኝ፥ አደረገኝ ብሎ ለሶስተኛ ሰው የሚነገር ወቀሳ፥ ቅሬታ።

ስሞተኛ ቅ ስሞታ መናገር የሚወድ።

ተሰማ ግ 1. ተደመጠ፥ ጆሮ ገባ። 2. በሌሎች ታወቀ። 3. ተቀባይነት፥ ተዳማጭነት አገኘ።

ተሰማው 1. የሃዘን፥ የቅሬታ ስሜት ገባው። 2. የኩራት፥ የንዴት፥ የበሽታ...፥ ስሜት ፈጠረበት።

ተሰሚ ቅ ተቀባይነት ወይም ተደማጭነት ያለው።

ተሳማ ግ ተዳረሰ፥ ተስፋፋ (ወሬው)።

ተስማማ ግ 1. ተዋዋለ፥ ውለታ ገባ። 2. ታረቀ፥ ቅሬታውን አስወገደ። 3. ጥሩ ሆነ፥ ተመቸ(አየሩ፥ ሃገሩ፥ ልብሱ፥...)። 4. አንድ ነገር ለመስራት አበረ፥ አንድ ሆነ። 5. ተቀበለ፥ እሺ አለ።

ተስማሚ ቅ ጥሩ፥ ምቹ (አየር፥ ሃገር፥ ልብስ፥...)።

አሰማ ግ 1. ነገረ፥ አሳወቀ። *አቤቱታውን አሰማ*። 2. እንዲደመጥ፥ ከጆሮ እንዲገባ አደረገ።

አሳማ ግ አዳረሰ፥ አስፋፋ (ወሬውን)።

አስማማ ግ 1. አስታረቀ፥ በሁለት ወይም ከዚያ በላይ ባሉ ሰዎች መካከል የነበረውን ቅራኔ፥ ጥል፥ ግጭት አስወገደ። 2. ለመሸጥ እንደሚፈልግ አሳወቀ ወይም ለገዥ፥ ለደላላ ነገረ። 3. ገዥና ሻጭን አንተ በዚህ ግዛ አንተ በዚህ ሽጥ አለ፥ አግባባ፥ ደለለ።

አስማሚ ስ አስታራቂ፥ ገላጋይ፥ ሽማግሌ።

ሰማ^2 ግ ሞቀ፥ ጋለ፥ ጋመ (ለምጣድ)።

አሰማ ግ አሞቀ፥ አጋለ፥ አጋመ።

***ሰማራ**

ስምሪት ስ 1.ለአንድ አይነት ስራ መሄድ ወይም መውጣት። 2.ግጦሽ መውጣት (የከብት)። 3.(ትራንስፖርት) የጉዞ መስመር ምደባ።

ተሰማራ ግ 1. ለአንድ አይነት ስራ ሄደ ወይም ወጣ። 2. ለግጦሽ ተነዳ፥ ተወሰደ (ከብት)።

አሰማራ ግ 1. ለአንድ አይነት ስራ ላከ፥ ሰደደ፥ መደበ። 2. ለግጦሽ አወጣ (ከብትን)።

ሰማንያ ስ 1. በሰባ ዘጠኝና በሰማንያ አንድ መካከል ያለ ቁጥር መጠሪያ በአሃዝ ሲፃፍ "፹" "80" ነው። 2. የጋብቻ ውል። 3. የሙት ሰማንያኛ ቀን፥ ተዝካር። ቅ 4. ብዛቱ ስምንት አስሮችን የሆነ።

ሰማንያ አወረደ የጋብቻ ውል አፈረሰ፥ ሚስቱን ፈታ።

የሰማንያ ሚስት ስ በጋብቻ ውል የተገባች ህጋዊ ሚስት።

የሰማንያ ባል ስ ህጋዊ ባል።

ሰማእት (ብ.ቁ. **ሰማእታት**) ስ ለሃገሩ፥ ለእምነቱ፥ ለሃይማኖቱ፥...መስዋእት የሆነ ሰው።

ሰማይ ስ ምድርን የከደናት የሚመስል ህዋ፥ ጠፈር፥ ከመሬት በላይ ከአድማስ እስከ አድማስ ያለው ቦታ።

ሰማይ አረገዘ ሊዘንብ የተቃረበ መሰለ።

ሰማይ ከበደ ሰማይ ጠቆረ፥ ደመና ሆነ፥ ጨፈገገ።

ሰማይ ሆኗል/ነክቷል በጣም ውድ ሆኗል (ዋጋው)።

ሰማይ ተደፋበት ተቸገረ፥ የሚያደርገውን አጣ።

ሰማይ ይነካል በጣም ረዥም ነው (ቁመቱ)።

ሰማይ ቤት ስ ከሞት በሃላ ነፍስ ትሄድበታለች ተብሎ የሚታመንበት ቦታ።

ሰማይ ጠቀስ ቅ ቁመቱ በጣም ረዥም የሆነ። *ሰማይ ጠቀስ ፎቅ አለው*።

ሰማይና ምድር ቅ የተራራቀ፥ የተለያየ፥ የማይመጣጠን።

የሰማይና የምድሩን ያህል በሰፊው፥ እጅጉን (ለሰላምታ)።

የሰማይ ስባሪ ግዙፍ፥ ትልቅ።

የሰማይ ቁጣ ስ የእግዚአብሄር ቁጣ።

ሰማያዊ ቅ 1. ሰማይ የሚመስል መልክ

ወይም ቀለም ያለው። 2. መለኮታዊ፣ ምድራዊ ወይም አለማዊ ያልሆነ። 3. በሰማይ የሚኖር።

ሰሜን ስ ፊቱን ወደ ፀሃይ መውጫ ካዞረ በስተግራ በኩል ያለ አቅጣጫ፣ የደቡብ ትይዩ።

ሰሜን ምስራቅ ስ በሰሜንና በምስራቅ መካከል ያለ ቦታ፣ አቅጣጫ፣ መስእ።

ሰሜን ምእራብ ስ በሰሜንና በምእራብ መካከል ያለ ቦታ፣ አቅጣጫ፣ ባህር።

የሰሜን ዋልታ ስ የምድር ሰሜናዊ ጫፍ።

ሰሜናዊ ቅ 1. በስተሰሜን አቅጣጫ ያለ ወይም የሚገኝ። 2. የሰሜን።

ሰም ስ 1. በቀላሉ የመቅለጥ ባህርይ ያለው የተለጠሰጠ ወይም የተጋገረ የማር ሰፈፍ። 2. የጣውላ ወለልን ለመወልወል የሚያገለግል ቅባት። 3. (ቅኔ) ላይ ላዩን የሚታይ ወይም ግልፅ ሆኖ ፊት ለፊት የሚተላለፍ ሃሳብ።

ሰምና ፈትል ሆኑ ተስማሙ፣ ተፋቀሩ፣ አንድ ሆኑ።

ሰም ለበስ ስ ግሱ እንደሰም ሆኖ የገባበት የቅኔ መንገድ።

ሰም ረገፍ ስ ከሰሙ ተለይቶ በወርቅ ብቻ የሚነገር ቅኔ።

ሰምና ወርቅ ስ ባለቤቱ ሁለት ሆኖ ባንድ አንቀፅ የሚነገር የቅኔ አይነት።

ሰምበሌጥ "**ሰንበሌጥ**"ን ተመ.

ሰምበር "**ሰንበር**"ን ተመ.

ሰምበቴ "**ሰነበተ**" ስር "**ሰንበቴ**"ን ተመ.

ሰምና ወርቅ "**ሰም**" ስር ተመ.

ሰሞን ስ 1. ስምንት ቀን። 2. ጥቂት ቀናት። *ለአንድ ሰሞን ወደ ውጪ ሄጄ ነበር።* 3. ቅርብ ቀን። *ሰሞኑን እመጣለሁ።*

ሰሙነ ህማማት ስ ከሆሳእና እሁድ ጀምሮ እስከ ቅዳሜ ስዑር ድረስ ያሉት ቀናት።

የሰሞን መሬት ስ ለቤተክርስቲያን አገልጋዮች (ለቀዳሾች) ይሰጥ የነበረ መሬት።

ሰሞነኛ ስ ከእሁድ እስከ እሁድ ቤተክርስቲያንን የሚያገለግል ተረኛ ቄስ ወይም ዲያቆን።

ሰረረ ግ ጠቃ፣ መታ፣ በፍትወት ስጋ ተገናኘ (ለእንስሳ)።

ሰሪያ ስ የእንስሳት ሩካቤ ስጋ።

ሰሪ ቅ የተጠቃች፣ የተሰረረች (ለእንስት እንስሳ)።

ተሰረረች ግ ተጠቃች።

አስረሽ ምችው ዘዬ ሆይታ፣ ዘፈን፣ የ[illegible] ሁኔታ፣ ፈንጠዝያ።

ሰረሰረ ግ 1. በቀጭኑ ቦረቦረ። 2. በሳ፣ ነደለ። 3. ቤትን፣ በርን ሰበረ (ለስርቆት)። 4. ውስጥ ውስጡን አመመ፣ ቆረቆረ(ለምሳሌ አፍንጫን)። 5. ውስጥ ለውስጥ ሄደ።

መሰርሰሪያ ስ ለመብሳት ወይም ለመቦርቦር የሚያገለግል መሳሪያ።

ሰርሳሪ ስ (ስድብ) ሌባ።

ተሰረሰረ ግ ተበረፈ፣ ተሰረቀ።

***ሰረሰረ**

ተንሰረሰረ ግ ተቀቀለ፣ በሰለ፣ ነፈረ፣ ፈላ።

አንሰረሰረ ግ በጣም ቀቀለ፣ አበሰለ፣ አነፈረ፣ አፈላ።

ሰረሰር ስ ውስጡ ክፍት የሆነ የአፍንጫ ወይም የአከርካሪ አጥንት።

ሰረቀ^1 ግ 1. የራሱ ያልሆነውን ነገር፣ ንብረት ደብቆ ወሰደ፣ ሞጨለፈ። 2. ጠቀሰ። *በአይኑ ሰርቆት ሄደ*። 3. ከትዳር ጓደኛው ደብቆ ከሌላ ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት ፈፀመ፣ ወይም በድብቅ የሌላን ሰው የትዳር ጓደኛ በግብረስጋ ተገናኘ።

ስርቆሽ ስ አንድን ነገር በሌብነት የመውሰድ ወይም የመፈፀም ድርጊት።

ስርቆሽ በር ስ ነገስታትና መኳንንት ከግቢያቸው ሲወጡና ሲገቡ እንዳይታዩ በሚፈልጉበት ጊዜ ብቻ ይገለገሉበት የነበረና ከዋናው የግቢ በር ይልቅ ከእይታ ገለል ባለው አቅጣጫ በኩል ይገኝ የነበረ በር።

ስርቆት ስ ሌብነት።

ስርቅ ብሎ ሄደ ሹልክ ብሎ ተሰውሮ ሄደ።

ስርቅ አድርጎ አየ ሳያዩት በትንሹ ዘወር ብሎ ተመለከተ።

ተሰረቀ ግ 1.ንብረቱን ተዘረፈ ወይም በስርቆት ተወሰደበት። 2. በድብቅ ወይም ባለቤቱ ሳያውቅ ተወሰደ (እቃው ንብረቱ)።

ተሰርቆ ሄደ ተደብቆ ሄደ።

ሰረቀ^2 ግ ወጣ፣ ብቅ አለ (ጨረቃ፣ ፀሃይ)።

ምስራቅ በፊደል ተራው ተመ.

ሰረበ^1 ግ በውስጡ ደም ያዘ፣ ቋጠረ (ስጋ፣ አይን፣...)።

ሰረበ^2 ግ ኳስን ወደ ተቃራኒው ቡድን ለጋ ወይም መታ (በመረብ ኳስ፣ በጠረጴዛ ኳስ፣... ጨዋታ ላይ)።

ሰርብ ስ ኳስን ወደ ተቃራኒው ቡድን ለማድረስ የሚለጋ የመጀመሪያ ምት (በመረብ ኳስ፣ በጠረጴዛ ኳስ፣...ጨዋታ ላይ)።

ሰረነቀ ግ ወደ ሰርን ውስጥ ገባ፡ አፈነ፡ ትን አለ።

ሰርንቅ አደረገ ግ ሰንግ፡ እንቅ አደረገ።

ሰረዘ ግ 1. በፅሁፍ ላይ አሰመረ፡ እንዳይነበብ አደረገ፥ አጠፋ። 2. ከፅሁፍ (ቃል፥ ሃረግ፥...) ስር መስመር አደረገ፡ አሰመረ (ከሌሳው ይበልጥ አትኩሮት እንዲደረግበት)። 3. አፈረሰ፡ አስቀረ፥ ተወ፥ ሻረ።

ሰረዝ ስ 1. ከፅሁፍ ስር እንዲሁም ከቃላት በስተኋላ ወይም በስተፊት በኩል በትንሹ አግድም የሚደረግ መስመር። 2. የሰርአተ ነጥቦች ምልክት (ለምሳሌ ነጠላ፡ ድርብ ሰረዝ)።

ሰርዝ ስ 1. እንዳይነበብ ለማድረግ ወይም ለማጥፋት በፅሁፍ ላይ የተሰመረ መስመር። 2. አፅንኦት ለመስጠት ከፅሁፍ ግርጌ ወይም ስር የተሰመረ መስመር።

ሰርዝ ድልዝ ስ ፅሁፍ እንዳይነበብ ለማድረግ ሲባል በፅሁፉ ላይ በተደጋጋሚ የተሰመረ መስመር እንዲሁም የነበረው ቃል ተፍቆ በሌላ ቃል የተተካ ፅሁፍ።

ተሰረዘ ግ 1.በፅሁፉ ላይ ተሰመረ፡ እንዳይነበብ ተደረገ፡ ጠፋ። 2. እንዲወጣ ተደረገ። *ከአባልነት ተሰረዘ።* 3. እንዲቀር ተደረገ፡ ተተወ። *የዛሬው የእግር ኳስ ጨዋታ ተሰርዟል።*

*ሰረየ

ሰርየት ስ ምህረት፡ ይቅርታ (የሃጢአት)።

ተሰረየ ግ ይቅርታ ተደረገ፡ ተተወ። *ሃጢአቱ ተሰረየለት።*

አስተሰረየ ግ ይቅርታ ወይም ምህረት አደረገ (ፈጣሪ)።

ሰረገ¹ ግ ድግስ ዳረ።

ሰርግ ስ 1. የጋብቻን በአል ለማክበር የሚደረግ ድግስና የአከባበሩ ስነ ስርአት። 2. (ዘይ.) ደስታ።

ሰርግና ምላሽ ደስታ፡ ፈንጠዝያ።

ሰርግ ቤት ስ የሰርግ ድግስ የተደረገበት ቤት።

የሰርግ ዘፈን ስ ለሰርግ የሚዘፈን ዘፈን።

ሰርገኛ ስ የሙሽራውና የሙሽራዋ አጃቢ፡ እድምተኛ፡ ታዳሚዎች።

ሰርገኛ [ጤፍ] ስ ነጭና ቀይ የተቀላቀለበት ጤፍ።

ተሰረገ ግ 1. የሰርግ ድግስ ተዘጋጀ። 2. በሰርግ ተዳረ፡ አገባ።

ሰረገ² ግ 1. ወደ ውስጥ ገባ፡ ዘለቀ፡ ሰመጠ። 2. ጎደጎደ (አይን)።

ሰርጎ ገብ ስ ለመሰለል፥ ለመምታት ወይም አደጋ ለማድረስ ማንነቱን ደብቆ ከጠላት ድርጅት፥ ሰፈር፥ አገር፡... የሚገባ ሰው።

ተሰረገረገ ግ ሰመጠ፡ ወደውስጥ ገባ፥ ተዋጠ።

አሰረገ ግ 1. አሰመጠ፡ ዋጠ። 2. ወደ ውስጥ አገባ፡ ወደ ውስጥ ወስዶ አስቀረ። 3. አከሰረ፥ አስጨረሰ፡ አቀለጠ (ገንዘብን)።

አስርግ ግ አክስር፥ አቅልጥ።

ሰረገላ ስ 1. ለመጓጓዣ የሚያገለግል በእንስሳት (በተለይ በፈረስ) የሚሳብ ጋሪ። 2. በድምድማት ላይ መሃል ለመሃል የሚጋደም ወፍራም እንጨት፥ ብረት፥ ግንዲላ።

ሰረገላ 1ኛ ፍ፡

ሰረገላ ቁልፍ ስ ባለዘንግ መክፈቻ ቁልፍ።(ስእሉን ቁልፍ ስር ተመ.)

ሰረገበ ግ ጠጣ፥ ጨለጠ።

ሰረጎደ ግ በመሰበር፥ በማጨራመት፥...አጎደጎደ።

ስርጉድ ቅ ጎድጓዳ፥ የተሰረጎደ።

ስርጉዳት ስ የጎደጎደ ቦታ።

ተሰረጎደ ግ በመሰበር፡ በመጨራመት፥ በመሟሸሽ ጎደጎደ።

*ሰረጨ

ስርጭት ስ በተለያዩ ቦታዎች የመድረስ፥ የመዳረስ ወይም የማዳረስ ሁኔታ፡ ተግባር።

ተሰራጨ ግ ተረጫ፡ ብዙ ቦታ ተዳረሰ፡ ተስፋፋ።

አሰራጨ ግ 1. አረጨ፥ ብዙ ቦታ አዳረሰ። 2. አከፋፈለ፡ በተነ። 3. አስተላለፈ (ዜናን በሬዲዮ፥ በጋዜጣ፥...)።

ሰረፀ ግ 1. በቀለ፡ ወጣ፡ ለመለመ። 2. ዘለቀ፥ ገባ። *ትምህርቱ ሰርፆታል።*

ሰራፂ ቅ የተገኘ፡ የወጣ።

አሰረፀ ግ 1. አስገኘ። 2. (በአእምሮ) ዘልቆ እንዲገባ፡ እንዲቀረፅ አደረገ።

*ሰረፈ

ተንሰራፋ ግ ተስፋፋ፡ ተደላደለ፡ ብዙ ስፍራ ያዘ።

አንሰራፋ ግ አስፋፋ፣ አደላደለ፣ ብዙ ስፍራ አስያዘ።

ሰረሳራ ስ በማንበር ግራና ቀኝ ከጉንጭ በላይ ያለ የሰውነት ክፍል(በእሉን ራስ ስር ተመ.)።

ሰረቲ(ሰረቴ) ስ እንቁ ያለውና እሾሃም የሆነ የእፅዋት አይነት፣ ቀሰተንቻ።

ሰራ[1] ግ 1. አደረገ፣ ፈፀመ፣ አከናወነ፣ አዘጋጀ። 2. አቋቋመ፣ አበጀ፣ ገነባ፤ አስገነባ። *ትምህርት ቤት ሰራ።* 3. ተበላሽቶ የነበረውን አስተካከለ፤ አበጀ፤ ጠገነ። 4. ፈጠረ፣ ፈለሰፈ። *ላውሮፕላንን መጀመሪያ የሰሩት ሁለት ወንድማማቾች ናቸው።* 5. ተግባሩን በትክክል ማከናወን ጀመረ፣ አከናወነ። *ሰዓቱ ይሰራል።*

_ ሰራት በ__አገር የተሰራ። *ጃፓን ሰራት የሆነ መኪና።*

የስራ አካላት መላ ሰውነት። *የስራ ላካላቴን ላምኛል።*

ሰራሰት መጥፎ ድርጊት ፈፀመበት።

ሲሰራት የዋለ በጣም ቆንጆ የሆነች።

ሰርቶ አደር ስ በማንኛውም የስራ መስክ ተሰማርቶ በሚያገኘው ገቢ የሚተዳደር ሰው።

መስሪያ ቤት ስ ማንኛውም የመንግስት ወይም የግል፤ የድርጅት ሰራዎች የሚከናዱበት፣ አመራር የሚሰጥበት ቦታ ወይም ቤት።

መሳሪያ ስ 1. አንድን ነገር ለመስራት፣ ለማምረት አጋዥ ሆኖ የሚያገለግል ማንኛውም እቃ። 2. የጦር መሳሪያ።

መሳሪያ መዘዘ ለማስፈራራት፣ ለመግደል፤... ጠበንጃ፣ ሽጉጥ አወጣ።

ሰራተኛ ስ 1. በተወሰነ የስራ መስክ ተሰማርቶ የሚያገለግል ሰው። ቅ 2. በስራው ላይ ብርቱ፤ ታታሪና ትጉህ የሆነ።

የሰራተኛ ማህበር ስ ሰራተኞች መብታቸውን ለማስከበር የሚያቋቁሙት ማህበር።

__ሰሪ ስራው __ን መስራት፤ ማበጀት የሆነ ወይም--ን በመስራት ላይ ያለ። *ፀጉር ሰሪ/ ቤት ሰሪ...።*

ስራ ስ 1. የአእምሮ ማሰላሰልንም ሆነ የጉልበት እንቅስቃሴን የሚሻና መደረግ፣ መፈፀም ያለበት ነገር፣ ተግባር። 2. አንድን ውጤት ለማስገኘት የሚደረግ የአእምሮ ማሰላሰልና የጉልበት እንቅስቃሴ፣ ክንዋኔ። 3. አገልግሎት፣ ጥቅም፣ ተግባር። ቅ 4. በአል ያልሆነ፤ የአዘቦት (ቀን)። *ዛሬ ስራ ነው፡ በአል ላይደለም።*

ስራ ለወጠ ወደሌላ መስሪያ ቤት ተዛወረ ወይም ሌላ ስራ ያዘ፣ ስራ ቀየረ።

ስራ ያዘ 1. በስራ ላይ ሆነ፤ በስራ ተጠመደ። 2. በአንድ አይነት ስራ ላይ ተሰማራ፣ ተቀጠረ፤ ተመደበ።

ስራ ፈታ 1. ሲሰራ የነበረውን ስራ አቆመ፣ ቦዘነ። 2. ስራ አጣ።

ስራ ፈት ቅ 1. ስራ አጥ፣ ስራ የሌለው። 2. ስራውን ትቶ በማይረባ ነገር ጊዜውን የሚያሳልፍ፣ ቦዘኔ።

ስራ ማስኬጃ ስ በአንድ መስሪያ ቤት ወይም ድርጅት፤ ...ውስጥ ለስራ ማከናወኛ የሚውል ገንዘብ።

ስራ አስኪያጅ ስ የአንድ መስሪያ ቤት ወይም ድርጅት ስራ መሪ፤ ሃላፊ።

ስራ አጥ ቅ የመስራት ችሎታ እያለው ስራ የሌለው ወይም ስራ ያላገኘ፣ ያልተቀጠረ (ሰው)።

ስራ አፈፃፀም ስ ሰራተኛ ስራውን የሚያካሂድበት፣ የሚፈፅምበት ሁኔታ ወይም ብቃት።

[የ]ስራ አፈፃፀም ቅፅ ስ በመንግስት መስሪያ ቤት የሰራተኞች የስራ አፈፃፀም ግምገማ ውጤት በተቀማጣሪው የሚመዘገብበት ቅፅ።

የስራ ልምድ ስ በአንድ የስራ መስክ ከስራው ሂደት የተገኘ እውቀት፣ ችሎታ።

የስራ ሰአት ስ እንደየመስሪያ ቤቱ ሁኔታ ሰራተኛ በስራ ገበታው ላይ የሚሆንበት፣ ስራ የሚሰራበት መደበኛው ጊዜ።

የስራ ሰው ስራ ወዳድ፤ ማጋጣ ያልሆነ።

የስራ ቀን ስ እንደየመስሪያ ቤቱ ሁኔታ መደበኛ ስራ የሚሰራበት፣ በአል ወይም እረፍት ያልሆነ ቀን።

የስራ ቋንቋ ስ መንግስታዊ መስሪያ ቤቶች የሚገለገሉበት ቋንቋ።

የስራ ዝርዝር ስ አንድ የስራ ክፍል፤ ሰራተኛ፤... እንዲያከናውናቸው በቅደም ተከተል የተመለከቱና የተመዘገቡ የስራ አይነቶች።

ስር ስ 1. የተሰራ፣ የተበጀ፤ የተመረተ፤ የተዘጋጀ። 2.የተሰራ፤ የተጎነጎነ(ፀጉር)።

ተሰራ ግ 1. ተደረገ፣ ተፈፀመ፤ ሆነ፤ ተከናወነ። 2. ተቋቋመ፣ ተበጀ፤ ተገነባ። 3.ተፈጠረ፣ ተፈለሰፈ፤ ተመረተ። 4. ተበላሽቶ የነበረው ተስተካከለ፣ ተበጀ።

አሰራ ግ 1.አቋቋመ፣ መሰረተ፣ አዘጋጀ፣ እንዲሰራ አደረገ። 2. አስጠገነ፤ የተበላሸው እንዲበጅ ወይም እንዲስተካከል አደረገ።

አሰሪ ስ 1. ስራን በበላይነት እየተቆጣጠረ የሚያሰራ ሃላፊ። 2. ሰራተኛን ቀጥሮ የሚያሰራ ድርጅት ወይም የድርጅት ባለቤት።

አሰራር ስ 1.የአዘጋጀት፣ የአደራረግ፤ የአዘገጃጀት መንገድ ወይም ሁኔታ። 2.አንድ መሳሪያ የሚንቀሳቀስበት ስርአት ወይም ሁኔታ።

የሳቧሉ ሞተር አሰራር ላይገባኝም።

ሰራ² ግ 1. ወሰነ፡ ደነገገ፡ ደነባ፡ ህግ አወጣ። 2. ሰበሰበ፥ አሰለፈ (ጦርን)። 3. መራ፡ አሰፈረ (የጦር ሰራዊትን)።

ስሬት ስ 1.ደንብ፡ ስርአት፡ ህግ። 2. የመሬት ይዞታ ደንብ፡ ስርአት፤ የመሬት ስሪትም ይባላል።

ስር ስ ደንብ፥ ህግ፥ ስርአት።

ተሰራ ግ 1. ተደነገገ፡ ደንብ ወጣ። 2.ተመራ፥ ሰፍሮ ያዘ፥ ተመደበ። *በአገራችን ወታደር ተሰርቷል።*

ተሰሪ ስ በቀድሞው ጊዜ በገባር ቤት ተመድቦ፡ ተመርቶ የሚቀመጥ ወታደር።

ሰራተኛ "ሰራ¹" ስር ተመ.

ሰራን ስ ነጭና ጠቆር ያለ ቀለም ያለው ዝንጉርጉር ፈረስ።

ሰራዊት ስ 1. በወታደራዊ ክፍል ውስጥ የሚገኝ አባላት በሙሉ። 2. ለአንድ አላማ በአንድ ቡድን ስር የተሰባሰበ ብዙ ህዝብ።

ሰርሳሪ "ሰረሰረ²" ስር ተመ.

ሰርብ "ሰረበ²" ስር ተመ.

ሰርተፊኬት ስ የምስክር ወረቀት።

ሰርን ስ የአፍንጫ ቦይ።

ሰርክ ስ 1. የቀን መጨረሻ፥ ምሽት። 2.ዘወትር፥ ሁልጊዜ።

የሰርክ ልብስ ስ የዘወትር ልብስ።

ሰርዲን ስ ለምግብነት የሚሆኑ የትናንሽ አሳዎች ዘር፡ ከዚሁ የተዘጋጀና በቆርቆሮ የታሸገ ምግብም ሰርዲን ይባላል።

ሰርዶ ስ ብዙ አንጓ ያለው፥ መሬት ለመሬት ስር እየሰደደ የሚሳብ የሳር አይነት።

ሰርገኛ "ሰረገ¹" ስር ተመ.

ሰርግ ዝ.ክ.

ሰርጥ(ሰርጥ) ስ ቀጭን፥ ጠባብ የእግር መንገድ።

ሰርፍ ስ 1. ባለዘርፍ የአልጋ ልብስ፥ ምንጣፍ። 2. የራስ ሳጥን የሚለብሰው ምንጣፍ፥ መጎናፀፊያ።

ሰሰነ **"ሴሰነ"** ን ተመ.

ሰሳ (ሰስ) ስ ኑሮው በገደላገደልና በተራራ የሆነ፥ ፍየል የሚመስል፡ ሲጋው የሚበላ ትንሽ የዱር እንስሳ (ለእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።

ሰቀለ ግ 1.አነሳ፥ ከፍ አደረገ፥ ወደላይ አራቀ። 2. አንጠለጠለ። 3. በመስቀል ላይ በመቸንከር ወይም አንገቱን በገመድ በማንጠልጠል ገደለ።

መስቀያ ስ ከእንጨት ወይም ከሽቦ ወይም ከፕላስቲክ፡... የተሰራ የልብስ ማንጠልጠያ፤ የልብስ መስቀያም ይባላል።

መስቀል ስ 1. ቀጥ ባለ እንጨት አናት አካባቢ ሌላ አጠር ያለ እንጨት በማጋደምና ሁለቱን በማያያዝ የሚዘጋጅ፡ በጥንት እስራኤላውያንና ሮማውያን ጊዜ ወንጀለኞችን አሰቃይቶ ለመግደል ያገለግል የነበረ የሰው መስቀያ። 2. ከላይ በተጠቀሰው ቅርፅ ከብረት፡ ከእንጨት፡... የሚዘጋጅ ክርስቶስ የተሰቀለበት መስቀል ምሳሌ፡ የክርስትና እምነት ተከታዮች ምልክት። 3. በመስቀል መልክ የተሰራ ማንኛውም አይነት ምልክት። 4. የክርስቶስ መስቀል ከተቀበረበት ቦታ መገኘቱን ምክንያት በማድረግ መስከረም 17 ቀን የሚከበር በአል። 5. የመስቀል ምልክት የሚደረግበት ወይም ማማተቢያ ጣት የሚያርፍበትና በአፍንጫ ትክክል የሚገኘው የግንባር ክፍል።

መስቀለኛ(መስቀልኛ) ቅ እንደ መስቀል ያለ።

መስቀለኛ መንገድ ስ በመስቀል ቅርፅ ወደተለያየ አቅጣጫ የተከፋፈለ መንገድ፡ መስመር።

መስቀለኛ ጥያቄ ስ አንድ ሰው የሰጠውን ቃል ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ከተቃራኒው ወገን በተለያየ መንገድ የሚቀርብ ጥያቄ።

የመስቀል ወፍ ስ 1. በመስከረም ወር የመስቀል በአል በሚከበርበት ሰሞን የምትታይ አነስተኛ ወፍ (ለእሉን ወፍ ስር ተመ.)። 2. (ዘይ.) አልፎ አልፎ ብቻ የሚታይ ሰው። *ምነው የመስቀል ወፍ ሆንክ?*

ሰቀላ ስ አግድምና ሞለል ብሎ የተሰራ ትልቅ ቤት፡ ዳስ፥ ድንኳን።

የሰቀላ መሬት ስ ርስት ያልሆነ፥ በቀድሞ ጊዜ አንድ ሰው ሲሾም ለመተዳደሪያ እንዲሆን የሚሰጠው መሬት።

ስቅለት ስ ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበትን እለት ምክንያት በማድረግ በየአመቱ ከፋሲካ በፊት ባለው አርብ ቀን የሚከበር በአል።

ስቅላት ስ ሰው አንገት ላይ ገመድ፡ ሸምቀቆ በማጥለቅና በማንጠልጠል የሚፈፀም የሞት ቅጣት።

ተሰቀለ ግ 1. ተንጠለጠለ፡ ወደላይ ከፍ አለ። 2. በገመድ ተንጠልጥሎ ሞተ።

አሳቀለ ግ 1. ነገርን፡ ጥልን አባባሰ፡ አጋነነ። 2. አዋደደ(ዋጋን)። 3. አሳጣ፥ በደሉን ነገረ (ለበላይ፥ ለፈጣሪ፡...)።

ሰቀሰቀ ግ አንድን ነገር ጠርሶ ለማንሳት ከስሩ ገብቶ ፈቀፈቀ፡ ሰረሰረ፥ ፈቀፈቀ፡ ጠረገ።

ሰቀሰቀበት በጦር ወይም በጩቤ ወጋው።

መሰቅሰቂያ(መሰቅሰቂት) ስ ከምጣድ ላይ እንጀራ ማሳቀቂያ ስንጥር እንጨት።

*ሰቀሰቀ

ስቅስቅ አለ ግ ምርር ብሎ አለቀሰ።

ተንሰቀሰቀ ግ ምርር ብሎ አለቀሰ፤ አነባ።

ሰቀቀ¹ ግ ሰቀጠጠ፤ ዘገነነ።

ሰቀቀን ስ 1. ተስፋ ያደረጉበትን ወይም ያሰቡትን በማጣት የሚሰማ የቅሬታ ስሜት፤ ሃዘን። 2. ናፍቆት።

ሰቀቀናም ቅ ቸጋራም፤ ስግብግብ፤ ስስታም።

ተሰቀቀ ግ በፍርሃት ወይም በስጋት ተሸማቀቀ፤ ተሰቃየ፤ ተጨነቀ።

ተሳቀቀ ግ 1. በፍርሃት ወይም በስጋት ተጨነቀ፤ ተሸማቀቀ። 2. ተስፋ ያደረገበትን፤ ያሰበውን አጣ።

አሰቃቂ ቅ በጣም አስከፊ፤ ዘግናኝ፤ አሳዛኝ፤ ሰቅጣጭ።

አሳቀቀ ግ 1. በፍርሃት፤ በስጋት አሰቃየ፤ አስጨነቀ። 2. አሳይቶ፤ አጓጉቶ ነሳ፤ ከለከለ።

ሰቀቀ² ግ መጠቀ፤ ወደላይ ከፍ እያለ ራቀ፤ ሄደ።

ሰቀቀናም "ሰቀቀ¹" ስር ተመ.

ሰቀቀን ዝ.ከ.

ሰቀዘ ግ ወጋ፤ ቀሰፈ ያዘ፤ አስጨነቀ(በህመም)።

*ሰቀየ

ስቃይ ስ በአካል ወይም በአእምሮ ላይ የሚደርስ ጭንቀት፤ መከራ፤ ህመም፤ ጉስቁልና።

ተሰቃየ ግ በህመም፤ በጉዳት፤ በጭንቀት፤ መከራ አየ፤ ስቃይ ተቀበለ።

አሰቃየ ግ አንገላታ፤ በህመም ወይም በጉዳት መከራ አሳየ፤ ስቃይ አደረሰ።

ሰቀጠ ግ ዋሸ፤ አታለለ።

ሲቃጢ ቅ ውሸታም፤ አታላይ።

ሰቀጠጠ ግ ዘገነነ።

ሰቅጣጭ ቅ የሚዘገንን።

ሲቃጢ "ሰቀጠ" ስር ተመ.

ሰቅ ስ 1. መታጠቂያ፤ ቀበቶ። 2. ማቅ፤ በርኖስ።

ሰቆረ ግ በሳ፤ ሸንቆረ፤ ነደለ።

መሰቅር ስ መብሻ፤ መሸንቆሪያ፤ ሹል ነገር።

መሰቆርት ስ የጆሮ መብሻ።

ሰቆቃ (ሰቆቃው) ስ ጩኸት፤ ዋይታ፤ የመረረ ለቅሶ፤ ሙሾ።

ሰበረ ግ 1. አነከተ፤ ቀለጠመ፤ አደቀቀ፤ ሸረፈ። 2. ተበላሸ፤ ልክ አልመጣ አለ(ለዜማ፤ ለግጥም)። 3. ጥሶ አለፈ። 4. ሰርስሮ ወይም በህገ ወጥ መንገድ ከፍቶ ገባ (ቤትን)። 5.ሰነከለ፤ አጎበጠ፤ አደቀቀ(በሽታ)። 6. አጨደ፤ ቆረጠ። *ባቄላ ሰበረ።*

ሰበር ሰካ አለ የቄንጥ አካሄድ ሄደ።

ሰበር ስ በአካሄድ ጊዜ የከብቶች እግር ያደቀቀው የሰንዴ፤ የገብስ፤... አገዳ።

ሰበር ስ አንድ ጉዳይ የመጨረሻ የፍርድ ውሳኔ ካገኘ በኋላ፤ መሰረታዊ የፍርድ ስህተት ሲኖረውና በጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ሲታዘዝ፤ ወይም በጠቅላይ አቃቤ ህግ አቤቱታ ሲቀርብበት እንደገና የሚታይበት ሁኔታ።

ሰባራ ቅ 1. ጉድለት ያለው፤ የተበላሸ፤ በትክክል የማይሰራ። 2. የአካል ስብራት ያለበት (ሰው)። 3. የተሸረፈ፤ በከፊል የተሰበረ። 4.ስባሪ፤ ሽራፊ።

ሰባራ ሰንጣራ ስ አነስተኛ፤ ጥቃቅን፤ መናኛ የቤት እቃ።

ስባሪ ቅ ሽራፊ፤ ቁራጭ፤ ጉማጅ።

ስብራት ስ 1. የመሰበር አደጋ። 2. የአጥንት መሰበር።

ሰባበረ ግ አደከመ፤ አደቀቀ (ሰውነትን)።

ስብርባሪ ቅ ቁርጥራጭ፤ ድቃቂ።

ስብርብር ያለ ያልተስተካከለ። *ስብርብር ያለ አረፍተ ነገር።*

ተሰበረ ግ 1. ነከተ፤ ደቀቀ፤ ተሰነጠቀ። 2. ስብራት ደረሰበት።

ተሰባሪ ቅ 1. በቀላሉ ሊሰበር የሚችል። 2.(ዘይ.) ሟች። *ሰው ተሰባሪ ነው።*

ተሰባበረ ግ አንድን ነገር ለማግኘት ተጣጣረ፤ ታገለ፤ ተራኮተ።

አሳበረ ግ በአቋራጭ መንገድ ሄደ።

ሰበሰበ ግ 1. ለቀመ፤ አጋበሰ፤ ወደራሱ አደረገ። 2. አከማቸ፤ በአንድ አደረገ። 3. አጠፈ፤ ከረተመ፤ መለሰ። ***እግሩን ሰበሰበ።*** 4. በስሩ አድርጎ አስተዳደረ፤ አኖረ (ዘመድን፤ ቤተሰብን)። 5. አጨደ፤ አስገባ፤ ከተተ(ሰብልን)። 6. ጠቅልሎ ወይም አጥፎ እንዳይንዘረፈፍ አደረገ(ልብስን፤...)። 7. ለጉባኤ ወይም ለውይይት ሰዎችን፤ ተሳታፊዎችን ጠራ፤ በአንድ አደረገ፤ ስብሰባውን መራ።

ሰበስብ (ስብሳብ) ስ በቤት ዙሪያ በስተውጭው በኩል ያለ ቦታ፤ ታዛ።

ሰብሳቢ ቅ 1. የሚያኖር፤ የሚያስጠጋ፤ ረዳት። ስ 2. የስብሰባ መሪ፤ ሊቀመንበር።

ሰብሳባ (ስብስብ) ቅ ቆጣቢ፤ የተቀጣ፤ ጨዋ።

ስብሰባ ስ ለአንድ አይነት ጉዳይ፤ ለውይይት፤ ...የሰዎች በአንድነት መገናኘት፤ ጉባኤ።

ስብሰባ ረግጦ ወጣ በስብሰባው አጀንዳ

ወይም በተዘረዘሩት ሃሳቦች ባለመስማማት ስብሰባውን ያለፈቃድ አቋርጦ ወጣ።

ስብሰባ ጠራ ጉባኤ ጠራ፤ ለውይይት ሰዎችን በተወሰነ ቦታና ሰዓት እንዲገኙ አደረገ።

ስብሰባውን ከፈተ ጉባኤውን ንግግር በማድረግ፥... ጀመረ።

ስብስብ ቅ ጥርቅም።

ተሰበሰበ ግ 1. ተለቀመ። 2. ተጠራቀመ፤ በአንድ ላይ ሆነ። 3. ተሸበሸበ። 4. በስብሰባ ላይ ተገኘ። 5. አረፈ፤ ተቆጥቦ ተቀመጠ። 6. ረዝሞ የነበረው ክትት አለ፤ ቅልብጭ አለ።

መሰብሰቢያ ስ መገናኛ ቦታ ወይም አዳራሽ።

ተሰባሰበ ግ ከያለበት መጣ፥በአንድ ላይ ሆነ፤ ተሰበሰበ።

አሰባሰበ ግ 1. በአንድ ላይ አደረገ፤ ከያለበት ሰበሰበ።2. ከሰዎች ሰበሰበ (መዋጮን)።

ሰበቀ¹ ግ 1. አማሰለ፥ በጠበጠ (እርጎን፥...)። 2. ወዘወዘ፤ ነቀነቀ(ጠርሙን)። 3. እሳትን ለማውጣት በመዳፎቹ መካከል እንጨትን፤ አስቶን አሽከረከረ፥ አሸ (ቀጠን ያለውን እንጨት ወፈር ካለው ላይ በማድረግ)።

መሰበቂያ ስ ሶስት ጣት ያለው ማማሰያ፤ መበጥበጫ እንጨት።



መሰበቂያ

ሰበቃ ስ ሁለት ነገሮችን የማፋጨት፥ የማፋተግ ሁኔታ፤ ስራ ወይም የሁለት ነገሮች መፋተግ፤ መፋጨት።

ሰበቀ² ግ የሚያጣላ፤ የሚያጋጭ ወሬን አቀበለ፤ አሳጣ።

ሰባቂ ቅ የሚያጣላ ወሬን አቀባይ፤ ወሬን እያቀበለ የሚያጣላ።

ስብቅ ስ ሰዎችን ለማጣላት ከአንዱ ወደ ሌላው ተወስዶ የሚነገር ክፉ ወሬ።

ስብቀኛ ስ ስብቅ የሚወድ፤ ወሬ አቀባይ።

ስብቀት ስ ስብቅ።

አሳበቀ ግ የሚያጣላ ክፉ ወሬ አቀበለ፤ ሰበቀ።

አሳባቂ ቅ የሚያጣላ ወሬን የሚያቀብል፤ ወሬኛ።

ሰበቀለ ግ ቆነጀ፤ ተዋበ፤ አማረ።

ስብቅል ቅ ቆንጆ፤ ውብ፤ የሚያምር።

***ሰበቀለ**

ስብቅል ቅ የተመሳቀለ።

ተሰባቀለ ግ ተመሳቀለ።

አሰባቀለ ግ አመሳቀለ።

ሰቢቃ "ሰበቀ¹" ስር ተመ.

***ሰበበ**

ሰበብ(ሰበብ) ስ ምክንያት፤ ብዙውን ጊዜ ማስተባበያ የሚሆን፤ ዋነኛ ምክንያት ያልሆነ።

ሰበብ አስባብ ስ የሆነ ያልሆነ ወይም በቂ ያልሆነ ምክንያት።

ሰበበኛ(ሰበበኛ) ቅ 1. ጥቂት ምክንያት፤ ሰበብ የሚፈልግ። 2. ደካማ፤ አቅመቢስ።

ተሳበበ ግ ተመካኘ።

አሳበበ ግ አመካኘ።

ሰበከ ግ 1. አስተማረ ሃይማኖት ወይም እምነትን። 2. አግባባ፤ አታለለ፤ አባበለ። 3. ኢ.ኦ.ተ.ቤ. ቄስ ወንጌል ከማንበቡ በፊት ዲያቆኑ ከዳዊት መዝሙር አዜመ

ምስባክ(ምስማክ) ስ 1. ኢ.ኦ.ተ.ቤ.፤ በፍትሐት፤ በቅዳሴ ወይም በሰዓት ጊዜ ወንጌል ከመነበቡ በፊት ዲያቆን ከዳዊት መዝሙር ውስጥ መርጦ የሚያዜመው ሶስት ስንኝ ያለው ጥቅስ። 2. ወንጌልን ማስተማሪያ፤ አዋጅን መንገሪያ ከፍ ያለ ቦታ ወይም መድረክ።

ሰበካ ስ አጥቢያ፤ ቀበሌ፤ አካባቢ፤ ሁሪያ (የቤተክርስቲያን)።

ሰባኪ ስ 1. ሃይማኖት አስተማሪ። ቅ 2.ሸንጋይ፤ ደላይ።

ስብከት ስ 1. ሃይማኖት ትምህርት፤ ህዝብ በተሰበሰበበት የሚሰጥ ወይም የሚነገር የሃይማኖት ቃል። 2.ለማግባባት፤ ለማባበል የሚነገር የመደለያ ወይም የመሸንገያ ቃል።

ተሰበከ ግ 1. የተሰጠውን የሃይማኖት፤ የርእዮተ አለም ትምህርት ተቀበለ። 2. ተታለለ፥ ተሞኘ፤ ተደለለ።

ሰበከት ስ የእንጀራ ወይም የቁርበት ጀርባ፤ እንጀራው ምጣድ ላይ ወይም ቁርበቱ መሬት ላይ የሚያርፍበት ወገን።

ሰበካ "ሰበከ" ስር ተመ.

ሰበዘ ግ ሰበዝን ሸጠ፤ ሸነጠ።

ሰበዘበት ሸጠበት (ጦርን፥...)።

ሰበዝ ስ የተሰነጠቀ ስንደዶና አክርማ በላዩ ላይ እየተጠመጠመበት የሚሰፋና የሚያያዝ ያልተሰነጠቀ ስንደዶ፤ የሰፌት ሳር፤ ሳሩም ሰበዝ ይባላል።

***ሰበደበደ**

ሰበድባዳ(ስብድብድ) ቅ ፈሪ፤ ቡቡ፤ ተርበድባጅ።

ተሰበደበደ ግ ፈራ፤ ባባ፤ ተርበደበደ።

ሰበጠረ(ሰባጠረ) ግ አመሳሰለ፡ አጠላለፈ።

ሰበጢራ(ሰበጠራ) ስ ከቀርከሃ፡ ከማሽላ አገዳ፡ ከሸምበቆና ከመሳሰሉት የሚሰራ የእንጀራ ቅርጫት ወይም ሰፌድ።

ስብጥር ቅ 1. ውስብስብ፡ ጥልፍልፍ። 2.ከየአይነቱ የተቀላቀለ፡ ቅልቅል የሆነ።

ተሰባጠረ ግ 1. ተጠላለፈ፡ ተወሳሰበ። 2.አልፎ አልፎ ጣልቃ ገባ፡ ተደባለቀ።

አሰባጠረ ግ 1. አስተሳሰረ፡ አጠላለፈ፡ አወሳሰበ። 2. አልፎ አልፎ አስቀመጠ፡ ጣልቃ አስገባ።

ሰባ ስ 1. በስድሳ ዘጠኝና በሰባ አንድ መካከል ያለ ቁጥር መጠሪያ። በአሃዝ ሲፃፍ ፸ ፡ 70 ነው። ቅ 2. ብዛቱ ሰባት አስሮችን የሆነ። *ሰባ ከብቶች።*

ሰባ^{2} ግ 1. ወፈረ፡ ደለበ፡ ሥጋም ሆነ (እንስሳ)። 2. ለማ፡ ዳበረ (መሬት)።

የሰባ መሬት ስ ለም የሆነ መሬት ወይም አፈር።

ስብ ስ 1. ሥጋ። ቅ 2. ለም፡ የዳበረ (መሬት)። 3. ወፍራም፡ ደንዳና (ለእንስሳት)።

ስባት ስ ውፍረት፡ ሥጋማነት (የእንስሳ)።

አሰባ ግ አወፈረ፡ አደነደነ፡ አደለበ።

አሰብቶ አራጅ ወዳጅ መስሎ፡ አዘናግቶ አጥፊ ወይም አድፍጦ፡ አድብቶ የሚጎዳ።

ሰባራ "ሰበረ" ስር ተመ.

ሰባሰገል "ሰብአሰገል" ን ተመ.

ሰባቂ "ሰበቀ^{2}" ስር ተመ.

ሰባት ስ 1.በስድስትና በስምንት መካከል ያለ ቁጥር። በአሃዝ ሲፃፍ ፯ ፡ 7 ነው። ቅ 2. ብዛቱ የአንድና የስድስት ድምር የሆነ። *ሰባት መፃሕፎች።*

ሰባኪ "ሰበከ" ስር ተመ.

ሰባጠረ "ሰበጠረ" ን ተመ.

ሰብል ስ እህል፡ የእርሻ ስራ ውጤት።

የሰብል ጊዜ ስ አዝመራ፡ እህል የሚሰበሰብበት ወቅት።

ሰብራዳ ስ ከጭቅና ጋር ያለ ሁለት የበሬ ጎድን።

ሰብሳቢ "ሰበሰበ" ስር ተመ.

ሰብሳባ ዝ.ከ.

ሰብቀኛ "ሰበቀ^{2}" ስር ተመ.

ሰብቅ ዝ.ከ.

ሰብአ ሰገል (ሰባሰገል) ስ ክርስቶስ በተወለደ ጊዜ ኮከብ እየመራቸው ከምስራቅ መጥተው እጅ መንሻ (ወርቅ፡ ከርቤ፡ እጣን) በማቅረብ የሰገዱለት ሰዎች መጠሪያ።

ሰብአ አይን "ሰብእ" ስር ተመ.

ሰብአዊ ዝ.ከ.

ሰብእ (ሰብ)

ሰብአ አይን ስ ሰላይ።

ሰብአዊ ቅ 1.የሰው ልጅ ሊያደርገው ወይም ሊሆን የሚገባው። 2. የሰው፡ የሰው ልጅ። *ሰብአዊ ባህርይ፥ ፍላጎት...።*

ሰብአዊ መብት ስ ሰው በሰውነቱ ሊደረግለት የሚገባ እንክብካቤ፡ ሊሰጠው የሚገባ ነፃነት።

ሰብአዊ መብት ረገጣ ስ ሰብአዊ መብትን መንፈግ፥ የመከልከል አድራጎት፤ በሰብአዊ ክብር ላይ የሚደረግ ጭቆና፥ ግፍ።

ሰብአዊ ርህራሄ ስ ለሰው ልጅ የሚደረግ ሃዘኔታ፥ በጎ ተግባር።

ሰብአዊ ርዳታ ስ የእለት ደራሽ የሆነ እንደ ምግብ፡ መጠለያ፡ መድሃኒት የመሳሰለ እርዳታ።

ኢሰብአዊ ቅ ጭካኔ፥ አረመኔነት የተሞላበት፡ በሰው ልጅ ላይ መደረግ የማይገባው።

ሰተረ^{1} ግ አሰጣ፡ ዘረጋ፥ ለፀሃይ ሰጠ።

ሰተረ^{2} ግ ሸከፈ፡ ሰበሰበ፡ በስርአት አስቀመጠ (እቃን)።

ተሰተረ ግ ተሸከፈ፥ ተሰበሰበ፡ በስርአት እንዲቀመጥ ተደረገ።

***ሰተተ**

ሰተቶ ስ ያለ ጋብቻ ውል ወይም ፈርማ ሴት ቤት ገብቶ የሚኖር (ወንድ)።

ሰታታ ቅ 1. ወግ ግብነት የሌለው፥ ለጥ ያለ (ሜዳ)። 2. ገላጣ፥ ዝርግ።

ሰታቴ ስ ትልቅና ሰፊ የሆነ የሸክላ ድስት።

ሰተት አለ ግ ያለችግር፡ ያለመሰናክል ወደ ውስጥ ገባ።

***ሰተፈ**

ተሳተፈ ግ የአንድ ስራ ተካፋይ ሆነ፡ የበኩሉን አስተዋፅኦ አደረገ፥ ድርሻውን አበረከተ፡ ተጋራ።

ተሳታፊ ቅ የአንድ ድርጊት ተካፋይ።

ተሳትፎ ስ በአንድ ስራ የመተባበር ወይም የመሳተፍ ተግባር።

አሳተፈ ግ በአንድ ስራ እንዲተባበር ወይም እንዲሳተፍ አደረገ።

***ሰነሰለ**

ሰንሰለት ስ እርስ በርስ ከተቆላለፉ ወይም ከተያያዙ ቀለበቶች የተዘጋጀ ለማሰሪያነት የሚያገለግል የብረት ገመድ።

ተሰናሰለ ግ እርስ በርስ ተቆላለፈ፡ ተያያዘ፡ ተቆራኘ።

ሰነቀ ግ ለጉዞ ወይም ለመንገድ የሚሆን ምግብ አዘጋጀ።

ስንቅ ስ ለጉዞ ወይም ለመንገድ የተዘጋጀ ምግብ ወይም የምግብ መግዣ ገንዘብ።

ስንቅና ትጥቅ ስ ለዘመቻ የሚሆን ምግብ፡ ገንዘብ፡ የጦር መሳሪያ፣…።

ተሰነቀ ግ ለጉዞ ፡ ለመንገድ ወይም ለዘመቻ የሚሆን ምግብ ተዘጋጀ።

ሰነቀረ ግ 1. ሻጠ፡ ሰካ። 2. ወሽመጥ ወይም ሰርዋዕ አገባ። 3. ወተፈ፡ ውሽል አገባ።

ተሰነቀረ ግ 1. ተሻጠ፡ ተሰካ፡ ተተከለ። 2. ያለአግባብ ጣልቃ ገባ።

ሰነበተ ግ 1. ለብዙ ቀን ወይም ጊዜ ቆየ፡ ኗረ ከረመ። 2. አዲስነቱን፡ ትኩስነቱን አጣ (ለመብል፡ ለመጠጥ)።

መሰንበቻ ስ መቆያ (ጊዜ፡ ቦታ)። 2.ሰሞኑን። *መሰንበቻዬን እመጣለሁ።*

ሰንበቴ (ሰምበቴ) (ኢ.ኦ.ተ.ቤ) ስ ሰንበትን ምክንያት በማድረግ ምእመናን በየሳምንቱ ጸበል፡ ጠላ፡ ቆሎ ወዘ. ቤተክርስቲያን ይዘው ሄደው የሚዘክሩት ግብር።

ሰንበት ስ የሳምንት መጨረሻና እረፍት የሚደረግበት ሰባተኛ ቀን፡ እሁድ።

ስንብት ስ 1. ከስራ መልቀቅ ወይም መባረር። 2. የመለያየት ስነ ስርአት ወይም የመለያያ ሰላምታ።

የስንብት ደብዳቤ ስ አንድ ሰው አንድን መስሪያ ቤት ለቆ ሲሄድ ወይም ከመስሪያ ቤት ሲባረር የሚጻፍለት ደብዳቤ።

ተሰነባበተ ግ የመሰነባበቻ፡ የመለያያ ቃል ተለዋወጠ።

ተሰናበተ ግ 1. ተባረረ፡ ተወገደ። 2. ደህና ሁን ተባብሎ ተለያየ። 3. ለቅሶ ደርሶ እግዜር ያጥናህ ብሎ ሄደ። 4.(ዘይ.) ሞተ።

የመሰናበቻ ግብዣ ስ የመሸኛ ግብዣ።

አሰነበተ ግ አቆየ፡ አከረመ።

አሰናበተ ግ 1. አባረረ፡ አስወገደ(ከስራ፣…)። 2. ሸኘ፡ እንዲሄድ አደረገ። 3. ለቅሶ የደረሱትን ሰዎች ሸኘ፡ ስንብት ሰጠ።

ሰነበጠ ግ በጣ፡ ቆረጠ፡ ቀደደ፡ ሰነጠቀ፡ ከፈለ (ብርቱካን፡ ሎሚ፡ ወዘተ.)።

ስንባጭ ቅ ትንሽ ቁራጭ፡ ክፋይ።

ተሰነበጠ ግ ተበጣ፡ ተቆረጠ፡ ተቀደደ፡ ተሰነጠቀ፡ ተከፈለ።

ሰንተረ ግ ሸንተረ፡ በጣ፡ ቀደደ።

ስንጥር ስ ሽንጥር።

ሰነነ ግ 1. በጣም ቀጠነ (ለሰውነት)። 2. በጣም ላመ፡ ደቀቀ (እህል፣…)።

ስናና ቅ 1.ቀጭን፡ ሰላላ፡ ቀጫጫ። 2. (ዘይ.) ሞኝ፡ ቂል፡ ፈዛዛ።

***ሰነኘ**

ስንኝ ስ የግጥም አንድ መስመር።

ተሰናኘ ግ ተስማማ፡ ተገጣጠመ (ስንኝ)።

አሰናኘ ግ አገጣጠመ፡ አስማማ (ለግጥም፡ ለዜማ)።

ሰነከለ ግ 1. ሰበረ(እግርን)። 2. አሰረ፡ ቀየደ፡ እንደልቡ እንዳይሄድ አደረገ።

ስንኩላ ቅ 1. እግሩ የተሰበረ፡ አንካሳ። 2.(ዘይ.) ደካማ፡ ብቁ ያልሆነ።

ስንኩል ዝ.ከ.

ተሰናከለ ግ ተጨናገፈ፡ ተጨናገረ፡ ተደናቀፈ፡ ተጓጎለ።

መሰናክል ስ 1. እንቅፋት። 2. (ዘይ.) አንድ ነገር በተሳካ ሁኔታ እንዳይሰራ የሚያደርግ ሁኔታ።

የመሰናክል ሩጫ ስ በየተወሰነ ርቀት ላይ የተደረደሩና ከፍታ ያላቸውን አግዳሚ እንጨቶች በዝላይ ተሻግረው እያለፉ የሚያደርጉት የሩጫ ውድድር።

አሰናከለ ግ 1. ጠለፈ፡ እንቅፋት ሆነ። 2. አጨናገፈ፡ አጨናገረ፡ አደናቀፈ፡ አስተጓጎለ።

ሰነዘረ^{1} ግ 1. በስንዝር ለካ፡ መጠነ። 2. በዱላ ወይም በእጅ ሊመታ ቃጣ። 3. (ዘይ.) ሰጠ (ሃሳብን)።

ስንዝር ስ የአውራ ጣት ጫፍ እስከ መካከለኛ ጣት ጫፍ ድረስ ሲዘረጋ ያለው የርዝመት መጠን ወይም ልክ።

ስንዝር የሚያህል አነስተኛ፡ ትንሽ።

ተሰነዘረ ግ ተሰጠ (ሃሳብ)።

ተሰናዘረ ግ ተላወሰ፡ ወዲያ ወዲህ ሄደ፡ ተንቀሳቀሰ።

መሰናዘሪያ ስ ወዲያ ወዲህ መላወሻ፡ መንቀሳቀሻ (ቦታ፡ ገንዘብ)።

አያሰናዝርም 1. አያላውስም፡ አያንቀሳቅስም። 2. አያወላዳም።

ሰነዘረ^{2} ግ ቆዳን ለመግፈፍ እንዲያመች ከጅራት እስከ ጉሮሮ፡ ከፊት እግር ጫፍ እስከ ኋላ እግር ጫፍ ቆዳውን በመስመር ሰነጠቀ።

ሰነደቀ ግ በአንድነት አሰረ፡ ሰበሰበ፡ አጠራቀመ (ነዶን)።

ስንድቅ ቅ በአንድ ላይ የተሰበሰበ፡ የታሰረ

ነዶ።

***ሰነዳ**

ስንዱ ቅ ዝግጁ።

ተሰናዳ ግ ተዘጋጀ።

መሰናዶ ስ ዝግጅት።

አሰናዳ ግ አዘጋጀ።

ሰነድ ስ ስለ አንድ ጉዳይ መረጃዎችን የያዘ ፅሑፍ፤ መዝገብ፤ ማስረጃ።

ሰነገ¹ ግ 1. በአፍንጫ ቀዳዳ ወደ ጎን ሽቦን ወይም ሳባን አስገባ (በከብት፤ በዶሮ)። 2. አጥብቆ፤ ጠምሮ ያዘ።

ሰናግ ስ በአፍንጫ ላይ የተሰካ ሳባ፤ ሽቦ (በከብት፤ በዶሮ)።

ተሰነገ ግ በሚያስጨንቅ ሁኔታ ውስጥ ገባ፤ ተያዘ።

ሰነገ² **(ሰነጋ)** ግ በቃሪያ ውስጥ ያለን ፍሬ አውጥቶ ሽንኩርት፤ ጨውና የመሳሰሉትን ነገሮች ጨመረ።

ስንግ ቃሪያ ስ ፍሬው ወጥቶ ሽንኩርት፤ ጨው፤...የገባበት ቃሪያ።

ተሰነገ(ተሰነጋ) ግ ፍሬው ከወጣለት በኋላ ሽንኩርት፤ ጨው፤...ገባበት (ቃሪያ)።

ሰነጋ¹ ግ የፈረስን፤ የበሬን፤ የበቅሎን፤ የወይፈንን፤...አካለ ዘር አኮላሸ፤ ቀጠቀጠ።

ሰንጋ ስ 1. የተቀጠቀጠ፤ የሰባ ድልብ በሬ። ቅ 2. የተኮላሸ፤ የተቀጠቀጠ (ከብት)።

ሰንጋ ፈረስ ስ የተቀጠቀጠ የሚጋለብ ፈረስ።

ሰንጎ መገን ስ 1. የግጥም አይነት፤ በተለይ ሽማግሌዎችን ለማሞገስ አዝማሪዎች በዜማ የሚያቀርቡት ግጥም። 2. የማሲንቆ ወይም የክራር ቅኝት አይነት።

ሰነጋ² **"ሰነገ²"** ን ተመ.

ሰነጠረ ግ በቀጭኑ ሰንጥቆ አወጣ (ለእንጨት)።

ስንጣሪ ቅ የተሰነጠረ፤ በቀጭኑ ተሰንጥቆ የወጣ (እንጨት፤...)።

ስንጥር ስንጣሪ።

ሰነጠቀ ግ 1. ከፈለ፤ አለያየ፤ ገመሰ። 2. እየጣሰ አለፈ። *አውሮፕላኑ አየሩን ሰንጥቆ ሄደ።* 3. ከፍተኛ ድምፅ፤ ጩሀት አሰማ። *እሪታውን ሰነጠቀው።* 4. መስመር አወጣ (የመንገድ)። *አውራ ጎዳና በዚህ በኩል ሰንጥቆ አስፋልት ሰራ።*

ሰንጣቃ ቅ ስንጥቅ።

ሰንጣቂ ቅ ከአንድ ነገር ተሰንጥቆ የወጣ ክፋይ።

ስንጥቅ ቅ መከፈል፤ መሰበር፤ መለያየት የጀመረ፤ የተሰነጠቀ፤ የነቃ (እቃ፤ግድግዳ፤...)። ስ 2. እየተሰበረ፤ እየተሰነጠቀ፤ እየተከፋፈለ ባለ ነገር ላይ የሚታየው ክፍተት፤ ንቃቃት።

ስንጥቅ አተረፈ የዋናውን ያህል አተረፈ።

ተሰነጠቀ ግ 1. ለመከፈል፤ ለመለያየት፤ ለመሰበር መንገድ አወጣ፤ መላቀቅ ጀመረ፤ ተገመሰ፤ ነቃ። 2. በሃይል ጮሀ (በሳቅ፤ በንግግር፤ በቁጣ)። 3.(ዘይ.) በጣም ዋሸ።

ተሰነጣጠቀ ግ ከውርጭ፤ ከድርቀት፤...የተነሳ ንቃቃት ወይም ስንጥቅ አወጣ (ለምሳሌ ከንፈር፤...)።

ሰነፈ ግ 1.ደካማ ሆነ፤ ብርታት፤ ሃይል አጣ። 2. አንድን ነገር ከመስራት፤ ከማድረግ ቸል አለ፤ ስራን ጠላ። 3. ደደበ፤ ትምህርት የማይገባው ሆነ።

ሰነፍ ቅ 1. አቅመቢስ፤ ደካማ፤ ቆራጥነት የጎደለው። 2. ቸልተኛ። 3. ስራ የማይወድ።

ሰነፍ መረቅ ስ ከጨው በስተቀር ቅቤና ቅመም ያልገባበት መረቅ።

ሰነፍ ምርት ስ ገለባው ከፍሬው ያልተለየ ወይም ያልጠራ ምርት።

ሰነፍ ቆሎ ስ እሳቱ ወይም ገለባው ሲያሽት በቀላሉ ከሚለቅ የገብስ አይነት የሚዘጋጅ ቆሎ።

ሰነፍ እርቅ ስ ዘላቂነት ወይም መሰረት የሌለውና በቀላሉ ሊፈርስ የሚችል እርቅ።

ስንፍና ስ ስራ ጠልነት፤ ቸልተኝነት።

ተሳነፈ ግ ሰነፈ፤ ተዘናጋ።

አሰነፈ ግ ቸል እንዲል አደረገ፤ አበዘነ።

አሳነፈ ዝ.ከ.

ሰነፈጠ ግ ሰረሰረ፤ ፈጀ፤ ለበለበ (አፍንጫን)።

ሰናፍጭ ስ ፍሬው እንደጎመን ዘር ያለና አፍንጫን የሚለበልብ ወይም የሚሰነፍጥ ቅመም።

ሰነፍ "ሰነፈ" ስር ተመ.

ሰናና "ሰነነ" ስር ተመ.

ሰናድር ስ ጥንታዊ የሆነ የጠበንጃ አይነት።

ሰናጋ ስ ጨርሶ እንዳይለያይ በልጥ የታሰረ ሰባራ አጥሬ ጨው።

ሰናፊል ስ ጥንታዊ ሱሪ፤ ተነፋነፍ።

ሰናፍጭ "ሰነፈጠ" ስር ተመ.

ሰኔ ስ ከግንቦት ቀጥሎ የሚመጣ የአመቱ አስረኛ ወር ስም።

ሰን ስ ከነሃስ ወይም ከመዳብ የተሰራ የእጅ መታጠቢያ፤ ኩስኩስት።

ሰንሰለት "*ሰነሰለ" ስር ተመ.

ሰንሰል ስ እጅብ ብሎ የሚበቅል የእፅዋት አይነት፤ ስሚዛ።

ሰንበሌጥ (ሰምበሌጥ) ስ ለቤት ክዳን የሚያገለግል ረዥም የሣር አይነት።

ሰንበር(ሰምበር) ስ 1. በሚሻክር፡ በሚጎረብጥ ነገር ላይ ከመተኛት ወይም በግርፊያ የተነሳ በአካል ላይ የሚታይ ምልክት፤ መስመር። 2. በጨርቅ ወይም በሌላ ነገር ላይ የሚደረግ የሰንበር ቅርፅ ያለው መስመር። 3. በእንስሳት ጀርባ መገጣጠሚያ ላይ የሚገኝ እንደ ደንደስ ያለ ወፍራምና ልሙጥ የሆነው ክፍል።

ሰንቡቴ "ሰነበተ" ስር ተመ.

ሰንበት ዝ.ክ.

ሰንቡላ [መራት] ስ በነሐሴ የሚወጣ ኮከብ። በተጨማሪ **ኮከብ ቆጠራ**"ን ተመ.

ሰንተራ ስ የወንጭፍ ድንጋይ አቃፊው ቆዳ።

ሰንካላ "ሰነከለ" ስር ተመ.

ሰንኪሎ (ሸንኪሎ) ስ ባልዲ።

ሰንኬቶ ስ ትንሽ ጣት ላይ የሚደረግ ቀለበት።

ሰንኮፍ(ሸንኮፍ) ስ 1.ልባስ፤ ክረቢት (ለምሳሌ ሰውነት ውስጥ የገባ መርፌ የተሸፈነበት)። 2. ያልተገረዘ የወንድ ብልት ሽፋን፤ ቆለፈት፤ ሸለፈት።

ሰንደል¹ ስ ሲያጨሱት ጥሩ ሽታ ያለውና በቀጭን ዘንግ መልክ የሚዘጋጅ የቤት ማጠኛ እንጨት፤ ነድ።

ሰንደል² ስ የነጠላ ጫማ አይነት፤ ሰንደል ጫማም ይባላል።

ሰንደቅ ስ የባንዲራ መሰቀያ ዘንግ።

ሰንደቅ አላማ ስ ባንዲራ።

የሰንደቅ አላማ መዝሙር ስ ባንዲራ ሲወጣና ሲወርድ የሚዘመር መዝሙር።

ሰንጋ "ሰነጋ²" ስር ተመ.

ሰንጎ መገን ዝ.ክ.

ሰንጠረዥ ስ 1. ልዩ ልዩ ጉዳዮችን በየመደቡ ለመመዝገብ አግድምና ቀጥ ቀጥ ተሰምሮበት የሚዘጋጅ ወረቀት፤ ሰሌዳ። 2. ባለ አራት ማእዘን የሆኑ ስድሳ አራት መደቦች ባሉት ዝርግ የእንጨት፣የፕላስቲክ፣... ሰሌዳ ላይ፣ ሁለት ሰዎች እያንዳንዳቸው በአሥራ ስድስት የመጫወቻ ቅርፆች አማካይነት ለአጨዋወቱ በተወሰነው ህግ መሰረት የሚጫወቱትና ስልትን የሚጠይቅ ጨዋታ፤ ቼዝ።



ሰንጠረዥ

ሰንጢ(ሴንጢ) ስ 1. ታጣፊ የሆነ አነስተኛ ቢላዋ። 2. (ዘይ.) ሀ. ብልጥ፤ ነገር አዋቂ፤ ለ. (ስድብ) ነገረኛ።

ሰንጣ ስ ወለል ያለ ሰፊ ሜዳ።

***ሰኘ**

ተሰኘ ግ ተባለ፤ ተሰየመ፤ ተጠራ።

አሰኘ ግ 1. አስባለ፤ አስጠራ፤ አሰየመ። 2. አስመኘ፤ አስፈለገ። *ምግብ አሰኝቶኛል*።

ሰኞ ስ በእሁድና በማክሰኞ መካከል ያለው ቀን ስም፤ ከእሁድ ጀምሮ ሲቆጠር የሳምንቱ ሁለተኛው ቀን።

ሰኣሊ "ሳለ²" ስር ተመ.

ሰኣልናከ (ሳሊንክ) ስ ለሰንበቴና ለማህበር ከሚጋገሩት ሁለት ዳቦዎች አንዱና ትንሹ (ሰኣልናከ የተባለው ጸሎት ከተባለ በኋላ ማህበርተኞቹ ብቻ የሚቀምሱት)።

ሰኣት ስ 1. ጊዜን በደቂቃ፤ በሰከንድ እየከፈለ የሚያሳይ የጊዜ መቁጠሪያ መሳሪያ። 2. የስድሳ ደቂቃዎች ርዝመት ያለው የጊዜ መጠን። 3. ጊዜ። *ብዙ ሰአት ፈጀ*። 4. ቀጠሮ፤ እለት ቀን፤ 5. ወቅት።

ሰኣት አደረሰ የተወሰነው የሚጠብቀው ሰአት እስኪደርስ ቆይቶ በላ፤ ወይም ቀን። *ቆይና ሰአት ሳይደርስህ ትሄዳለህ*።

ያለሰኣት ያለወቅቱ፤ ያለጊዜው።

ሰኣት ማሰሪያ ስ የእጅ ሰአትን እጅ ላይ ለማሰር ከብረት ወይም ከቆዳ… የሚሰራ ማሰሪያ።

ሰኣት ቆጣሪ ስ በእጅ፣ በጠረጴዛ ወይም በግድግዳ ሰአት ላይ ከደቂቃ ቆጣሪው አነስ ያለውና ሙሉ ሰአትን የሚጠቁመው አመልካች ቀስት ወይም ዘንግ።

ሰኣት እላፊ ስ ከተወሰነው ሰአት በኋላ መዘዋወር ወይም መንቀሳቀስ የሚከለከልበት የጊዜ ገደብ።

ሰኣት እላፊ ተነሳ የሰአት እላፊ አዋጅ ተሻረ፤ ቀረ።

ሰኣት እላፊ ታወጀ ከተወሰነ ሰአት በኋላ መዘዋወር የሚከለከል የጊዜ ወይም የሰአት ገደብ ህግ ወጣ።

ከሰኣት [በሃላ] ተው.ግ. ከቀትር፤ ከእኩለ ቀን በኋላ።

ከሰኣት በፊት ተው.ግ ከቀትር፤ ከእኩለ ቀን በፊት።

ሰኣታት (ሳታት) (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ስ ካህናት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሌሊት በዜማ የሚያደርሱት ፀሎት።

ሰኣታት ቆመ የሰኣታትን ፀሎት በዜማ

አደረሰ፡ ፀሰየ።

የሰአታት መፅሃፍ ስ የሰአታት ፀሎት መፅሃፍ።

ተሲአት (ተሲያት) ስ ቀትር።

ሰከም

ሰከም ሰከም አለ ግ ጠደፍ ጠደፍ እያለ ሄደ።

ሰከረ ግ በአልኮል መጠጥ፣ በእፅ፣... ምክንያት ስሜቱን፣ የሚሰራውን መቆጣጠር አቃተው።

ሰካራም ቅ 1. አልኮል መጠጥ አዘውትሮ የሚጠጣ፣ ጠጪ። 2. አልኮል መጠጥ ጠጥቶ የሰከረ።

ስካር ስ የአልኮል መጠጥን ወይም ሌላ አስካሪ ነገርን በመውሰድ የሚፈጠር ራስን ያለመቆጣጠር ስሜት።

ተሳከረ ግ 1. በአንድ ላይ በመሆንና አልኮል በመጠጣት ሁሉም ሰከረ። 2. ተምታታ፣ ተዘበራረቀ።

አሰከረ ግ ስሜትን መቆጣጠር እንዲሳን አደረገ፣ ራስ አዞረ (መጠጥ፣ እፅ፣...)

አስካሪ ቅ የሚያሰክር (መጠጥ)።

አሳከረ ግ አዘበራረቀ፣ አምታታ።

ሰከሰከ ግ 1. ተስገበገበ፣ ጠራርጎ በላ። 2. ሰረረ። 3. ሸቀሸቀ፣ አመቀ፣ ሰገሰገ።

ሰከነ ግ 1. ወረደ፣ ዘቀጠ፣ ረጋ (የቡና አተላ)። 2. ጨመተ፣ ረጋ አለ፣ እደብ ገዛ። 3. የተለመደ፣ የታወቀ ሆነ። *የሰከነ ቃል መጠቀም ያስፈልጋል።*

ሰካ ግ 1. ሻጠ፣ ተከለ፣ አገባ። 2. አጠለቀ።

ስኬት ስ የአላማ ወይም የድርጊት ክንዋኔ በየፋ ሁኔታ እንደታቀደው መፈፀም።

ስኬታማ ቅ የተሳካ፣ ጥሩ ውጤት ያለው።

ሰኪ ቅ የሚሰካ፣ የሚገጣጠም።

ሰኪ ሳህን ስ የሚገጣጠም ሳህን።

ተሰካ ግ ተሻጠ፣ ተተከለ፣ ተሸጎጠ።

ተሰካካ ግ ተገጣጠመ።

ተሳካ ግ ተሟላ፣ ተቃና፣ ተስተካከለ፣ በሚፈለገው መልክ ተከናወነ።

አሳካ ግ 1. አቃና፣ አሟላ፣ በሚፈለገው መልክ እንዲከናወን አደረገ። 2. አቀናበረ፣ አስተካከለ (ለአረፍተ ነገር፣ ለንግግር)።

ሰኮና "ሸሆና" ን ተመ.

ሰኮንድ(ሴኮንድ) ስ የሰአት አነስተኛ ክፍልፋይ። አንድ ሰኮንድ የደቂቃ አንድ ስድሳኛ ነው።

ሰኮንድ ቆጣሪ ስ በእጅ፣ በጠረጴዛ ወይም በግድግዳ ሰአት ላይ ከሙሉ ሰአት ቆጣሪው ረዥም የሆነውና የሰኮንድን መጠን አመልካች የሆነው ቀጭን አመልካች ዘንግ።

*ሰወለለ

ተንሰዋለለ ግ ተንቀዋለለ።

አንሰዋለለ ግ አንቀዋለለ።

ሰወረ ግ 1. ደበቀ፣ ጋረደ፣ ሸፈነ፣ ሸሸገ። 2. አይንን አወረ፣ ጋረደ።

ሰዋራ ቅ ሽሽግ፣ ድብቅ (ቦታ)።

ስውር ቅ ሽሽግ፣ ድብቅ፣ የማይታይ።

ስውር ስፌት ስ ክሩ እንዳይታይ ሆኖ የተሰፋ ስፌት።

ተሰወረ ግ 1. ተደበቀ፣ ተሸሸገ። 2. ታወረ።

ሰዋ ግ 1. አረደ። 2. ሰጠ (ህይወትን ለሃገር፣ ለሃይማኖት)። 3. አቀረበ፣ ሰጠ (መስዋእትን ለአምላክ)።

መስዋእት ስ 1. ለአምላክ የሚሰዋ፣ የሚቀርብ ስጦታ። 2. (ክር.) ስጋ ወደሙ።

መስዋእት ሆነ ህይወቱን አሳልፎ ሰጠ (ለአገሩ፣ ለእምነቱ)።

መስዋእት አደረገ ሰዋ፣ መስዋእት አቀረበ።

መስዋእት ከፈለ ለአላማው፣ ለእምነቱ መስዋእት ሆነ፣ ለህይወቱ ሳይሳሳ ታገለ።

ተሰዋ ግ ህይወቱን አሳልፎ ሰጠ (ለሃገሩ፣ ለአላማው፣ ለሃይማኖቱ)።

ሰዋራ "ሰወረ" ስር ተመ.

ሰዋሰው ስ የቃላት አመሰራረትንና የአረፍተ ነገር አሰካክ ስርአት ወይም ህግ። *የሰዋሰው ስህተቶችን አርም።*

ሰው ስ 1. ማሰብና ማመዛዘን የሚችል፣ ሰብአዊ ፍጡር። 2. በሶስተኛ መደብ የሚጠራ፣ ሌላ ግለሰብ። *ሰው መጣ /ሰው ነገረኝ/ ሰው እንዳይሰማ።* 3. ዘመድ፣ አጋር፣...። *ሰው ስለሌለኝ ስራ ላይ ሆኜ ቀረሁ።*

ሰው ሆነ ራሱን ቻለ፣ በረታ፣ አእምሮ ገዛ፣ ጎበዝ ሆነ።

ሰው ለየ 1. አወቀ። *ህፃኑ ሰው ለይቷል።* 2. አዳላ። *ይህም ጥቅም ሆኖ ሰው ይለይበታል።*

ሰው አይሆንም 1. ከደረሰበት ሃዘን፣ ብስጭት፣ ጉዳት፣ መከራ፣... የተነሳ በጣም ይጎዳል። 2. ለቁም ነገር፣ ለጥሩ ውጤት አይበቃም።

ሰው አይደለም በጣም መጥፎ ሰው ነው።

ሰው መሳይ በሸንጎ በሩቅ ለሚያውቀው ጥሩ ሰው መስሎ የሚታይ።

ሰው ሰራሽ ቅ የተፈጥሮ ያልሆነና ሰው

የሰራው::

ሰው በላ /በሌ ቅ ጨካኝ፡ አረመኔ::

ሰው በሰው በሌላ ሰው እርዳታ::

ሰው ጤፉ ሰው የሚንቅ፡ ያለ እኔ ማን አለ የሚል::

ሰውዬ 1.አንድ ሰው:: *አንድ ሰውዬ ውጭ ቆሟል::* 2. አንተ ሰው (ለጥሪ)::

የሰው የሌላ ግለሰብ:: *መኪናው የኔ አይደለም፤ የሰው ነው::*

የሰው ልክ አያውቅም ሰውን ያለአግባብ ይዳፈራል::

የሰው መጨረሻ ነው በጣም ጥሩ ሰው ነው::

የሰው ነጭ ታየ ቁጥሩ የበዛ ሰው ታየ፡ ወይም ተገኘ::

የሰው ሃይል ስ ሰራተኛ:: *ለስራው መፋጠን ተጨማሪ የሰው ሃይል ያስፈልጋል::*

የሰው ልጅ ሰው የተባለ ፍጡር በጠቅላላ::

የሰው አይን ባየው ነገር ላይ ጉዳት፡ ጠንቅ የሚያደርስ ወይም የሚያስከትል አይን::

የሰው አይን በላው ሞተ ወይም ሌላ ጉዳት ደረሰበት (በቡዳ፡... ምክንያት)::

የሰው አገር ሰው ባይተዋር፡ እንግዳ::

የሰው ዘር ሰው የተባለው ፍጡር ሁሉ::

ሰውነት ስ ገላ፡ አካላትን፣[illegible] የሰው ገላ

ሰውነቱ ላመ ከድካም የተነሳ ሰውነቱ ደቀቀ፡ ዛለ::

ሰውነቱን ጠበቀ ለሰውነቱ እንክብካቤ ወይም ጥንቃቄ አደረገ::

ሰውኛ ስ ሰው ያልሆነውን ነገር እንደሰው በማናገር ወይም የሰው ባህርይ በመስጠት የሚነገር የዘይቤ መንገድ::

ሰውር [መሬት] ስ በሚያዝያ የሚወጣ የከዋክብት አይነት፤ በተለምዶ "ኮከብ ቆጠራ" ን ተመ.

ሰየ ግ ሳመጀ፡ ተመኘ::

ሲያቴ ቅ ስግብግብ፤ ሁሉ ነገር የሚያምረው::

ሰየመ ግ 1. ስም ሰጠ፤ ስም አወጣ:: 2. አስቀመጠ፤ አዘጋጀ፤ አቀረበ::

ስያሜ ስ 1. ስም፡ መጠሪያ:: 2. የመሰየም ስራ፡ አንድን ነገር ወይም ሃሳብ የሚወክል ቃል የመፍጠር ተግባር::

ስያሜ ቃላት ስ ለሙያ ወይም ለአዳዲስ ዕንስ ሃሳቦች በሃገርኛ ቋንቋ መጠሪያ የመስጠት ስርአት፡ ተግባር::

ተሰየመ ግ 1. ስም ወይም መጠሪያ ወጣለት:: 2. ተቀመጠ (ለስብሰባ፡ ለፍርድ፡...)::

***ሰየረ (*ሴረ)**

ሴራ ስ አድማ፡ ዱለታ::

ሴራ ቆረጠ አድማ አደረገ፡ ዶለተ::

ሴራ ጠነሰሰ ተንኮል፡ ሴራ፡ አድማ ወጠነ ::

ሴረኛ ቅ አድመኛ፡ አድማ አቀነባባሪ::

አሴረ ግ አደመ፡ ዶለተ፡ ሴራ ጠነሰሰ::

ሰየፈ ግ 1. በጎራዴ ወይም በሰይፍ መታ፡ ቀነጠሰ፤ በጠሰ:: 2. አጋደመ፡ በሰያፍ አደረገ::

ሰያፍ ቅ 1. አግድም፡ የጎንዮሽ የሆነ:: 2. (ዘይ.) በማስታከክ የተነገረ፡ ፊት ለፊት ያልሆነ (ለንግግር)::

ሰይፍ ስ በሁለት በኩል ስለት ያለው ቀጥ ያለና ከወደጫፉ ሾጣጣ የሆነ የጦር መሳሪያ::



ሰይፍ

ተሰየፈ ግ በሰይፍ ተመታ፡ ተቀላ፡ ተቆረጠ::

አሰየፈ ግ በሰይፍ ቅጣት ወይም በሰላች ሆነ::

ሲያቴ "ሰየ" ስር ተመ.

ሰያፍ "ሰየፈ" ስር ተመ.

ሰይጣን ስ 1. ተግባሩ መጥፎ የሆነ፡ እርኩስ መንፈስ፡ ጋኔን፡...:: 2. (ዘይ.) ክፉ፡ መጥፎ (ሰው)::

ሰይጣኑ መጣ ተናደደ፡ ተቆጣ::

ሰይጣን አትሁንብኝ እንድናደድ፡ እንድቆጣና መጥፎ ስራ እንድሰራ ምክንያት አትሁንብኝ::

ሰይጣን የለከፈው ክፉ፡ መጥፎ (ሰው)::

ሰይጣን ያጋለው/የጋለበው ሰይጣን የተጠናወተው፡ እኩይ ሰው::

የሰይጣን ቁራኛ ቅ ክፉ፡ መጥፎ::

የሰይጣን ቁራጭ ቅ ክፉ፡ መጥፎ፡ አሳሳች፡ ሰይጣን የሆነ (ለሰው)::

የሰይጣን ዶሮ ስ ባህር ውስጥ ጠልቆ መቆየት የሚችልና ጠቃጠቆነት ያለው የአሞራ አይነት::

የሰይጣን ፈረስ ቅ ግልፍተኛ፡ ቁጡ፡ ጠብ ጫሪ::

ሰይጣናም ቅ ተናዳጅ፡ ግልፍተኛ፡ ቁጡ::

ሰይፍ "ሰየፈ" ስር ተመ.

ሰደረ ግ ደረደረ፡ በረድፍ፡ በተራ አስቀመጠ::

ተሰደረ ግ ተደረደረ፤ በረድፍ፡ በተራ ተቀመጠ::



1. ፊት
2. እልቅት
3. ደረት
4. ጡት
5. ብብት
6. እምብርት
7. በገድ
8. ሙሃሂት
9. እምስ
10. ፋርንትት
11. ቁላ
12. ጭን
13. ጉልበት
14. ቅልጥም
15. የእግር ጣት
16. አንገት

የሰውነት ክፍሎች



1. ትከሻ
2. ጀርባ
3. ሽንጥ
4. ዳሌ
5. ቂጥ
6. ክርን
7. ታፋ
8. ቋንጃ
9. ባት
10. ቁርጭምጭሚት
11. ተረከዝ
12. ኮቴ
13. ማጅራት
14. ብራኳ
15. ክንድ

ሰደርያ ስ ከኮት ስር፡ ከሸሚዝ በላይ የሚለበስ እጅጌና አንገትጌ የሌለው ልብስ።

ሰደቃ ስ 1. ገበታ፡ መሶብ። 2. የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ለድሆች የሚያበሉት ተዝካር።

ሰደበ ግ ዘለፈ፡ ወረፈ፡ አዋረደ፡ አረከሰ፡ ከፍ ዝቅ አድርጎ ተናገረ።

ስድብ ስ ዘለፋ፡ ለማዋረድ ወይም ለማሳነስ የሚነገር መጥፎ ቃል።

ስድብ ቀመሰ ተሰደበ።

በስድብ ተለቀቀበት በጣም ሰደበው፡ የስድብ ናዳ አወረደበት።

ተሰደበ ግ ተዘለፈ፡ ተዋረደ።

ተሳደበ ግ አዋረደ፡ ዘለፈ።

ተሳዳቢ ቅ አዋራጅ፡ መሳደብ ልማዱ የሆነ።

አሰደበ ግ ለመዋረድ፡ ለመነቀፍ ምክንያት ሆነ።

አሰዳቢ ቅ ለመሰደብ ምክንያት የሚሆን (ተግባር፡ ጠባይ)።

ሰደደ ግ 1. ላከ። 2. አባረረ፡ አሰናበተ። 3.ለቀቀ፡ ፈታ። 4. ከተተ፡ አገባ። *በሰው ቁስል እንጨት ሰደደበት እንዲሉ።* 5. የሰደድ እሳትን አቀጣጠለ ወይም ለኮሰ።

ሰደድ እሳት ስ ሃይለኛ የሆነና ጫካ ውስጥ ወይም ቁጥቋጦና ደረቅ ሳር ባለበት የሚነሳ እሳት፡ ቃጠሎ።

ስደት ስ በመባረር፡ በፖለቲካ ወይም በሌላ ችግር ምክንያት አገርን ለቆ መሄድ፡ ፍልሰት።

ስደተኛ ስ አገሩን ያለፈቃዱ ለቆ በሌላ አገር የሚኖር ሰው።

ስድ ቅ 1. ልቅ፡ ያልተከፋፈለ፡ ሰፊ (ቤት)። 2. (ስድብ) ባለጌ።

ስድ ንባብ ስ ግጥም ያልሆነ ንባብ።

ስድ አደግ ስ ባለጌ።

ተሰደደ ግ በፖለቲካ ወይም በሌላ ችግር ምክንያት አገሩን ለቆ ሄደ።

ተሳደደ ግ ተባረረ።

አሳደደ ግ 1. እየተከታተለ አባረረ። 2. ስራዬ ብሎ አንድን ነገር ተከታተለ።

አሳዳጅ ቅ አንድን ነገር ከመውደዱ ወይም ከመፈለጉ የተነሳ ስራዬ ብሎ የሚከታተል።

ሰደፍ^{1} ስ የጠመንጃ እግር፡ ሳት (ስእሉን ጠመንጃ ስር ተመ.)።

ሰደፍ^{2} ስ እንቁ ወይም ሉልን የምትወልድ የባህር ፍጥረት።

ሰገሰበ ግ ተስገበገበ፡ ተጣደፈ፡ ቸኮለ (አንድን ነገር ለማግኘት ወይም ለማድረግ)።

ስግሳባ ቅ ቸኩል፡ ስግብግብ።

ሰገረ ግ በአጭር እርምጃ እየፈጠነ በማይደናቀፍ አካሄድ ሄደ፡ ፈሰሰ (ስለበቅሎ፡ ስለፈረስ)።

ሲጋር ቅ ሲሄድ ወይም ሲራመድ ጋላቢውን የማያደናቅፍ (ብዙውን ጊዜ ለበቅሎ)።

ሰገራ ስ (ሰው) አይነ ምድር።

ሰገራ ወጣ ተፀዳዳ።

ሰገሰገ ግ 1. ጠቀጠቀ፡ በክፍት ቦታ ሞላ፡ ሰካ። 2.ጠቀጠቀ፡ አጠጋጋ (የጨርቁን ጥለት ወይም ማግ ለመቋጠት)። 3. በብዛት አስገባ፡ ሞላ።

ስግስግ ቅ ጥቅጥቅ፡ በደንብ ተጠጋግቶ የተሰራ።

ተሰገሰገ ግ 1. ተጠቀጠቀ፡ በክፍት ቦታ ገባ፡ ተሰካ። 2. በብዛት ገባ፡ ሞላ።

***ሰገበገበ**

ስግብግብ (ሰገብጋባ) ቅ ስስታም፡ ቅቅታም።

ተስገበገበ ግ በጣም ጓጓ፡ ሰፍ አለ (ለምግብ ወይም ለሌላ ነገር)።

አስገበገበ ግ በጣም አጓጓ፡ አንሰፈሰፈ፡ ሰፍ አደረገ። *ምን ያስገበግብሃል? ቀስ ብለህ ታገኘዋለህ።*

ሰገባ ስ አፎት፡ የሰይፍ ማህደር።

ሰገብጋባ "***ሰገበገበ**" ስር "**ስግብግብ**"ን ተመ.

ሰገነት ስ 1. የፎቅ ቤት በረንዳ። 2. በአካባቢው ካሉት ነገሮች ሁሉ በጣም ከፍ ብሎ የተሰራ ቦታ (ለመመልከቻ የሚሆን)። 3. ባለአንድ ፎቅ የገጠር ቤት።

ሰገደ ግ 1. ተንበረከከ፡ አጎነበሰ፡ ተደፋ (ለአምላክ ሀሎት፡ ምስጋና ለማቅረብ)። 2. ተሸነፈ፡ እጅ ሰጠ፡ የሌላውን የበላይነት አወቀ። 3. (ዘይ.) አጎበደደ።

ስግደት ስ 1. ለአምላክ ክብርና ምስጋናን ለማቅረብ፡ ይቅርታን ለመጠየቅ እየፀለዩ የሚያደርጉት የማጎንበስ፡ የመንበርከክ ስርአት። 2. በክርስትና ሃይማኖት መሰረት በሁማማት ውስጥ በተለይም የስቅለት እለት እየሰገዱ የሚያከናውኑት የፀሎት ስርአት።

አሰገደ ግ ሰጥ ለጥ አድርጎ ገዛ።

***ሰገደደ**

ስግዳዳ ቅ 1. ደባቃ፡ ሰዋራ (ቦታ)። 2. ጎንባሳ፡ ጎበጥ ያለ። 3. ረባዳ።

ስግድድ አለ ግ 1. ረባዳ ሆነ። 2. ጎንበስ፡ ጎበጥ አለ።

ሰገድ ስ ከወይራ ጋራ ተመሳሳይነት ያለው የዛፍ አይነት።

ሰገገ ግ ቀጥንና ረዥም ሆነ (አንገቱ)።

ሲጋጋ ቅ አንገተ ረዥም።

ስግግ አለ ግ በጣም ቀጥኖ ረዘመ (አንገቱ)።

ስግግ አደረገ ግ መዘዘ፡ አስረዘመ (አንገቱን)።

አሰገገ ግ አንገቱን መዘዘ፡ አስረዘመ።

ሰገጠ ግ 1. ሸለመ፡ ቀመቀመ፡ አስጌጠ፡ ዘመዘመ። 2. አጠቆረ፡ ቋጠረ፡ አስከፋ (ፊትን)።

ሰገጥ ስ ዝምዝማት፡ ጌጥ፡ ቅምቅማት፡ ሽልማት፡ ንቅሳት (የካባ፡ የቀል፡…)።

ተሰገጠ ግ ተዘመዘመ፡ ተቀመቀመ፡ ተሸለመ።

ሰገጥ¹ (ሰጎጥ) ስ መሬት ውስጥ የተተከለና ለመንቀል የሚያስቸግር ድንጋይ፡ የዛፍ ስር፡…።

ሰገጥ² "ሰገጠ" ስር ተመ.

ሰጋ ግ ፈራ፡ መጥፎ ነገር ይደርስል ብሎ ጠረጠረ፡ ተጨነቀ።

ስጉ ቅ ብዙ ጊዜ አንዳች መጥፎ አደጋ፡ ክፉ ነገር፡… ይደርስል ብሎ የሚፈራ።

ስጋት ስ ፍርሃት፡ ጥርጣሬ።

አሰጋ ግ አስፈራ፡ አስጨነቀ።

አስጊ ቅ አደገኛ፡ አስፈሪ።

ሰጋር "ሰገረ" ስር ተመ.

ሲጋጋ "ሰገገ" ስር ተመ.

ሰግላባ "ሰገለበ" ስር ተመ.

ሰግዳዳ "*ሰገደደ" ስር ተመ.

ሰጎን ስ አንገቱና እግሮቹ ረጃጅሞች፡ አካሉም ግዙፍ የሆነና የማይበር በአፍሪቃ የሚገኝ የአእዋፍ አይነት (ሰእሉን ወፍ ስር ተመ.)።

ሰጎደ ግ 1. መታ፡ ጠበቀ። 2. አጎደጎደ፡ ሰረጎደ። 3. አበጀ (ጋሻን)።

ሰጎጥ "ሰገጥ¹" ን ተመ.

ሰጠ ግ 1. አደለ፥ አቀበለ። 2. ቸረ፡ ለገሰ። *አገሬ ለተቸገረ ይሰጣል*። 3. ሸለመ፡ በቋሚነት አበረከተ። 4. ተመቸ፡ ጥሩ ሆነ። *ቀሚሱ ለቅርጫት ኳስ ጨዋታ የሰጠ ነው*። 5. ከፈለ፥ በለውጡ ሌላ እንዲወስድ አደረገ። ለመፅሃፉ አስር ብር ብሰጠው አያዋጣኝም አለ። 6. አስገኘ። *ፀሃይ ብርሃን ትሰጣለች*። 7. መስዋእት አደረገ፡ መስዋእትነት ከፈለ። *ለአገሩ ህይወቱን ሰጠ*። 8. አዋለ፡ ለመስዋእትነት አዘጋጀ። *ህይወቱን ለመልካም ተግባር የሰጠ ነው*። 9. አስረከበ። *ደብዳቤውን ዛሬ ሰጠሁት*። 10. እንዲደርሰው አደረገ። *መልእክቱን ሰጠው*። 11. ነገሩን አሳወቀ፥ ገለፀ፥ እንዲያውቅ አደረገ። *መልስ ሰጠ*። 12. አሳየ፡ ገለፀ፡ ነገረ። *ምልክት ሰጠ*። 13. እንዲያዝ አደረገ። *ስልጣን ሰጠ*።

እሰጥ አገባ ስ 1. የቀድሞ ጊዜ የሙግት ወይም የክርክር መንገድ። 2. አስፈላጊ ያልሆነ ሙግት፡ ጭቅጭቅ።

ሰጭ ቅ ቸር፡ ለጋስ፡ ደግ።

ስጦታ ስ 1.ገፀ በረከት። 2. ችሎታ።

ሰጪ ቅ 1. ቸር፡ ለጋስ። 2. አዳይ፡ አከፋፋይ (በካርታ ጨዋታ)።

ተሰጠ ግ 1. ታደለ። 2. ተበረከተ። 3. እንዲደርስ ተደረገ፡ ተነገረ። *ምስጋና ተሰጠው*።

ተሰጥኦ ስ 1.ልዩ ችሎታ። 2. (እ.ኦ.ተ.ቤ.) በቤተ ክርስቲያን ህዝቡ ከዲያቆኑና ከቄስ እየተቀበለ የሚያዜመው የቅዳሴ ዜማ፡ ፀሎት።

ሰጠመ "ሰመጠ" ን ተመ.

ሰጠሰጠ ግ 1. ደበደበ፡ ገረፈ፡ መታ፡ ወቀጠ። 2. በሃይል ጣለ፡ ወረደ። *ዝናቡ ትናንት ሲሰጠስጠው አደረ*። 3. በብዛት ፃፈ።

***ሰጠጠ**

ሲጢጥ አለ ግ በር ሲከፈትና ሲዘጋ ማጠፊያዎች የሚያሰሙትን አይነት ድምፅ አሰማ።

ሲጢጥ አደረገ ዝ..ከ.

ተንሲያጠጠ ግ ሲጢጥ የሚል አይነት ድምፅ ሰጠ ወይም አሰማ።

አንሲያጠጠ ግ ሲጢጥ የሚል ድምፅ አሰማ።

***ሰጣ**

ስጥ ስ ፀሃይ እንዲመታው የተዘረረ ወይም የተዘረጋ እህል።

ተሰጣ ግ ፀሃይ ላይ ተዘረረ ወይም ተዘረጋ (እህል፡ ልብስ፡…)።

አሰጣ ግ ለፀሃይ ሰጠ፡ ዘረረ፡ ዘረጋ (እህልን፡ ልብስን፡…)።

ማስጫ ስ 1. እህልን ፀሃይ ላይ ለማስጣት የሚያገለግል እንደሰፌድ፡ ኪሻ፡… ያለ እቃ። 2. ልብስ የሚሰጣበት ገመድ፡ ሽቦ፡…።

አሰጣጣ ግ ሰጡን አገለባበጠ።

ሰጥ¹

ሰጥ ለጥ አለ ግ ተሸቆጥቁጦ፥ እሺ፥ አሜን ብሎ ተገዛ፡ ተዳደረ።

ሰጥ² "ሰጠ" ስር ተመ.

ሰጥር ስ ቀጭን የጎድን አጥንት።

ሰጭ "ሰጠ" ስር ተመ.

ሰፈረ¹ ግ 1. ለካ፥ መጠነ (መጠኑን ለማወቅ)። 2. በተለያዩ መስፈሪያዎች እየለካ፡ እየመጠነ ሰጠ። 3. ከአፍ እስከገደፉ ጢም አድርጎ ሞላ፡ ከሚገባው በላይ ጨመረ፡ ቀዳ፡…።

በሰፈረው ቁና ተሰፈረ ለፈፀመው ክፉ ስራ ዋጋውን አገኘ፤ ተከፈለ።

መስፈሪያ ስ መለኪያ፥ መመዘኛ እቃ (እንደ ቁና፥ ሰሃን፥ ሜትር፥ …ያሉ)።

መስፈርት ስ መሟላት ያለበት አስፈላጊ ነጥብ፤ መለኪያ። *እዚህ መስሪያ ቤት ለመቀጠር የምታሟላቸው መስፈርቶች አሉ።*

ስፍር ቅ 1. የተለካ፥ የተመጠነ። ስ 2. ልክ፥ መጠን።

ስፍር ቁጥር የለውም እጅግ በጣም ብዙ ነው።

ተሰፈረ ግ 1. ተለካ፥ ተመጠነ። 2. ተቀበለ (የቀለብ እህልን)።

ሰፈረ² ግ 1. መኖሪያ ቦታ ያዘ፤ ኗሪ ሆነ። 2 አረፈ፤ ተቀመጠ። 3. ቆጥ ላይ ወጣ፥ ማደሪያውን ያዘ (ዶሮ)። 4. ተጻፈ፤ ተመዘገበ።

ሰፈረበት 1. ለመምታት፤ ለመደብደብ ያዘው፤ ጣለው፤ እላዩ ላይ ወጣ። 2. ያዘው፤ አደረበት። *ጋኔን ሰፈረበት።*

ሰፈራ ስ ቀድሞ ከነበሩበት መኖሪያ ተነስቶ ሌላ ቦታ የመኖር ድርጊት።

ሰፈራ ጣቢያ ስ ከሌላ ቦታ የመጡ ሰዎች እየሰሩ እንዲኖሩበት የተዘጋጀ ቦታ።

ሰፈረተኛ ስ የአንድ አካባቢ መንደር ኗሪ (ህዝብ)።

ሰፋሪ ቅ ቀድሞ የነበረበትን መኖሪያ ለቆ በሰፈራ ሌላ መኖሪያ ቦታ ይዞ የሚቀመጥ።

ሰፈር ስ 1. በጉዞ ላይ ያሉ ሰዎች ወይም ወታደሮች ጊዜያዊ መኖሪያ። 2. የመኖሪያ አካባቢ።

ስፍራ ስ ቦታ።

ስፍራ ያዘ 1. ቦታ አጣበበ። 2. መቀመጫ ቦታ አግኝቶ ተቀመጠ።

ተሳፈረ ግ መኪና፥ አውሮፕላን፥ መርከብ ላይ ወጣ (ለጉዞ)።

ተሳፋሪ ስ ተጓዥ፤ መንገደኛ (በመጓጓዣ)።

አሰፈረ ግ 1. ቦታ አስያዘ፤ የመኖሪያ ቦታ፥ ክልል ሰጠ። 2. ጻፈ፥ መዘገበ።

አሳፈረ ግ 1. ለማጓጓዝ ጫነ (አውሮፕላኑ፥ መርከቡ፥…)። 2. ተሳፋሪን፤ መንገደኛን ሸኘ (መኪና፥ ባቡር፥… ውስጥ እስኪገባ)።

***ሰፈሰፈ**

ስፍሳፋ ቅ 1. ገብጋባ። 2. ለለመጠን ችኩል፥ ጉጉ።

ስፍስፍ አለ ግ 1. በጣም ተንገበገበ። 2. ተንዘፈዘፈ፥ ተንቀጠቀጠ። 3. ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ። 4. ተሰቃየ።

ተንሰፈሰፈ ግ 1. ተንገበገበ፥ ጓጓ። 2. ተንዘፈዘፈ፥ ተንቀጠቀጠ፥ ተርገበገበ። 3. ተንሰቀሰቀ፤ ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ። 4. የስቃይ፥ የህመም ስሜት ክፉኛ ተሰማው።

አሰፈሰፈ ግ አቆበቆበ፥ ተዘጋጀ፤ በጉጉት ጠበቀ።

አንሰፈሰፈ ግ 1. አንዘፈዘፈ፥ አንቀጠቀጠ። 2. አንገበገበ።

ሰፈነ ግ ሞላ፤ ከዳር እስከ ዳር ሆነ። *ፀጥታ ሰፈነ።*

አሰፈነ ግ ከዳር እስከ ዳር እንዲሆን አደረገ፤ ሞላ። *በሃገሪቱ ሰላምን አሰፈነ።*

ሰፈፈ ግ ከፈሳሽ ነገር ላይ ከላይ ሆኖ ሳይሰጥም ተገኘ ወይም ታየ።

ሰፌፍ ስ የነገር አሰር፤ ምጣጭ፤ የጠጅ ገፈት (ስም የሚሆን)።

ሰፌፍ የለውም እንከን፥ ነውር፥ ክፋት የለውም።

ተንሳፈፈ ግ 1. ከላይ ሆነ፥ ዋኘ፥ ከፈሳሽ ነገር ላይ ሆኖ ሳይሰጥም ከላይ ቀረ ወይም ታየ። 2. አንዣበበ፥ በአየር ላይ በረረ። 3. የነበረበት መስሪያ ቤት የመዋቅር ለውጥ በማድረጉና በአዲሱ መዋቅርም ባለመታቀፉ ከስራ ተወገደ።

ተንሳፎ ቀረ ከማንኛውም ወገን ሳይሆን ቀረ።

አሰፈፈ ግ ሰፈፈ፤ ተንሳፈፈ።

አንሳፈፈ ግ 1. አሰፈፈ፥ በላይ አደረገ፥ ሳያሰጥም ቀረ። 2. በአየር ላይ አበረረ።

ሰፌ "ሰፋ²" ስር ተመ.

ሰፋ ስ ቀጥና መሰል ብሎ የሚበቅል፥ ለዘንግ የሚሆን የእፅዋት አይነት፤ ጠፍ፤ ሰማያም ይባላል።

ሰፋ² ግ 1. በመርፌና በክር እያያዘ፤ ጠቀመ፤ ዘመዘመ፤ ወሰወሰ (ለምሳሌ ልብስን)። 2. አዘጋጀ፤ አበጀ፥ ሰራ (ሰፌድን፥ ጫማን፥ …በመርፌና በክር፤ በስንደዶ፤… በማያያዝ)። 3. ወጋ፥ ሰነገ፤ አስጨነቀ፤ ቀሰፈ። *ውጋት ሰፍቶ ያዘኝ።*

ሰፌታ ስ የመሶብንና የሌላውንም የስፌት ስራ በደንብ የምታውቅ ባለሙያ።

ስፌት ስ 1. የመስፋት ስራ ወይም ሙያ። 2. ልብስ፥ ጫማ ወዘተ. በመርፌና በክር የተያያዘበት ቦታ። 3. እንደመሶብ፥ ሙዳይ፥ ሰፌድ የመሳሰሉና ብዙውን ጊዜ ከስንደዶ፤ ከአክርማ፥ ከገራምጣ የሚዘጋጅ የቤት እቃ።

የስፌት መኪና ስ ጨርቃ ጨርቅን፥ ቆዳን፥ ሸራን፥… ለመስፋት የሚያገለግል ዘመናዊ መሳሪያ።

አሰፋ ግ በልኩ እንዲሰፋለት አደረገ (ልብስን)።

ሰፋ^{2} ግ 1. በጎን ወይም በወርድ ወይም ዙሪያውን መጠኑ ጨመረ፥ አደገ፥ ሰፊ ሆነ፥ ተለቀ። 2.ከልክ በላይ ሆነ፥ ተለጠጠ (ለልብስ፥ ለጫማ፣…)። 3. ተንበረቀቀ (ቀዳዳው፣ ክፍተቱ፥ አፉ)። 4. ጨመረ፥ አደገ፥ ከፍ አለ። *እውቀቱ ሰፋ / ድርጅቱ ሰፋ።*

ሰፊ (ብ.ቁ. **ሰፋፊ**) ቅ 1. የተንጣለለ፥ ዙሪያው፥ ወርዱ ወይም ጎኑ ስፋት ያለው። 2. ከልክ በላይ የሆነ (ልብስ፥ ጫማ ፥…)። 3. ቦርቃቃ፣ ቀዳዳው፥ ክፍተቱ፥ አፉ የሰፋ። 4. ጥልቅ፥ ብዙ ፡ ከፍ ያለ፣ ትልቅ። *ስለመዛግብተ ቃላት አሰራር ሰፊ እውቀት አለው።*

ሰፊው ህዝብ ስ ብዙሃኑ ህዝብ።

ስፋት ስ 1. ወርድ ወይም ጎን። *ሜዳው ስፋት እንጂ ቁመት የለውም።* 2. አንድ ነገር በቁመቱና በጎኑ በአጠቃላይ የሚይዘው፥ የሚጠቀልለው ቦታ። 3. ብዛት፥ ጥልቀት።

[የ]ስፌት እቃ ስ እንደ ሰፌድ፣ መሶብ፥… ያለ ከሰንደዶ፣ ከአክርማ፣ከገራምጣ የሚሰራ የቤት እቃ (ስእሉን በሚቀጥለው ገፅ ተመ)።

ተስፋፋ ግ 1. ተንሰራፋ፣ ተመቻቸ፣ ብዙ ቦታ ይዞ ተቀመጠ፥ ተደላደለ። 2. አደገ፣ ተጠናከረ፣ ተደራጀ። *ኢንዱስትሪ በሃገሪቱ ተስፋፍቷል።* 3. ተዛመተ፥ ተራባ፥ ተዳረሰ፥ ተሰራጨ። *በሽታ ተስፋፋ።*

ተስፋፊ ቅ የራሱን ክልልና ድንበር አልፎ ግዛትን የማስፋፋት እቅድ ወይም ፖሊሲ ያለው።

አሰፋ ግ 1. በጎን ወይም በወርድ ወይም ዙሪያውን መጠኑን ጨመረ፥ አሳደገ፥ አተለቀ። 2. ከልክ በላይ አደረገ፥ ለጠጠ (ለልብስ፥ ለጫማ፥…)። 3. አምበረቀቀ። 4. ጨመረ፥ አሳደገ፥ከፍ አደረገ (ለእውቀት፣ ለድርጅት፥…)። 5. የእንጀራ ሊጥን በምጣድ ላይ አፈሰሰ፥ አበረ።

አስፋፋ ግ 1. አሳደገ፥ ከፍ አደረገ። *የንግድ ድርጅቱን አስፋፋ።* 2. አብራራ፥ ተነተነ። 3. አዛመተ፣ አራባ። *ወሬውን አስፋፋ/ በሽታን አስፋፋ።*

ሰፋሪ "**ሰፈረ**^{2}" ስር ተመ.

ሰፋድል ስ በማህፀን ውስጥ ሽል የሚቀመጥበት ስስ የሆነ ከረጢት፣ ከርታስም ይባላል።

ሰፌድ ስ ከአክርማ፥ ከሰንደዶና ከገራምጣ የሚሰራና ለእህል ማበጠሪያና ማንፈሻ እንዲሁም ከምጣድ ላይ ለእንጀራ ማውጫ የሚያገለግል ስፌት (ስእሉን የስፌት እቃ ስር ተመ.)።

ሰፌድ እግር ቅ ውስጥ እግሩ ጠፍጣፋ የሆነ (ሰው)።

ሰፍሳፋ "***ሰፈሰፈ**" ስር ተመ.

ሰፍነግ ስ 1. ውሃን በውስጡ መቋጠር የሚችልና በባህር ውስጥ የሚገኝ እንደ ስፖንጅ ያለ የእፅዋት አይነት። 2. ስፖንጅ።

ሱ የ"**ሰ**" ፊደል ካእብ ዘር።

ሱልጣን ስ በእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ ሃይማኖታዊ ስልጣን ያለው ሹም ወይም ለሹሙ የሚሰጠው የማእረግ ስም።

ሱሬት ስ በጉንጭ የሚያዝ ወይም በአፍንጫ የሚሸተት የትምባሆ ዱቄት።

ሱሪ ስ እያንዳንዱን እግር ለየብቻ እንዲሸፍን ሆኖ የተዘጋጀ ከወገብ እስከ ቁርጭምጭሚት ወይም እስከ ጉልበት የሚደርስ ልብስ (ስእሉን ልብስ ስር ተመ.)።

ሱስ ስ 1. አንዴ ከተለመደ በሃላ በየጊዜው ውል የሚል ወይም የሚያሰኝ እንደትምባሆ፥ ቡና የመሳሰሉት ነገሮች ልማድ፣ አመል፣ አምሮት። 2. (ዘይ.) ልማድ፥ አመል፣ ፍቅር (አንድን ነገር የማድረግ)።

ሱሰኛ ቅ ሱስ ያለበት፣ ሱስ የያዘው።

ሱቅ ስ ልዩ ልዩ ሸቀጣሸቀጦች ወይም እቃዎች የሚሸጡበት ቤት፣ መደብር።

ሱቅ በደረቴ ስ ሸቀጣ ሸቀጦችን በሻንጣ ወይም በአነስተኛ ሳጥን እየያዘ በመዘዋወር የሚሸጥ አነስተኛ ነጋዴ።

ሱባኤ ስ 1. ለተወሰነ ጊዜ ከሰው ተለይቶ የሚደረግ ፆም፥ ፀሎትና ስግደት፣ ቀኖና። 2. (ቤ.ክህ.) የሰባት ቀን ጊዜ።

ሱባኤ ገባ/ያዘ 1.ለተወሰነ ጊዜ ከሰው ተለይቶ ፆምና ፀሎት፥ ስግደት አደረገ፣ ቀኖና ያዘ። 2. ከሰው ተለይቶ ተቀመጠ፥ ተደበቀ።

ሱቲ ስ ዝንጉርጉርና መናኛ የጨርቅ አይነት።

ሱጎ "ስጎ" ን ተመ.

ሱፋጮ ስ ስለት ያለው ድንጋይ፣ ሻፎ።

ሱፍ^{1} ስ ቢጫ አበባ ያለውና ፍሬው የሚበላ ዘይት የሚወጣው ሰብል። ከዚሁ ሰብል የሚገኘው ነጭ ፍሬም ሱፍ ይባላል።

የሱፍ ውሃ ስ ከተወቀጠና ከተቀቀለ የሱፍ ፍሬ የሚዘጋጅ፥ ለመጠጥነትና ለማባያነት የሚያገለግል ፈሳሽ።

ሱፍ^{2} ስ ከበግ ፀጉር የሚሰራ ጨርቅ።

ሲ የ"**ሰ**" ፊደል ሳልስ ዘር።

ሲ - "ስ-" ን ተመ.

ሲሊንደር ስ ሞላላ ቅርፅ ያለውና ቡታጋዝ፥ አክስጅን፥…የሚሞላበት ከብረት የተሰራ እቃ።

ሲሳ ስ ጫጩትን፥ ርግቦችን፥ ወፎችን እየጠለፈ የሚበላ የጭልፊት አይነት፣ አሞራ። (ስእሉን አሞራ ስር ተመ.)።

ሲል

የበፊት እቃዎች።

1


2


3

4


5


6


7


9


10


1.ሙሙ
2.ወንፊት
3.ሙዳይ
4.መሶብ ወርቅ
5.ቃጤ

6.ሌማት
7.ቁና
8.አገልግል
9.እርቦ
10.ሰፌድ

ሲል ኣለ ግ ታንቆ፡ ተንጠልጥሎ፥ ተሰቅሎ ሞተ።

ሲሚንቶ (ሰሚንቶ) ስ ከኖራና ከሸክላ አፈር በፋብሪካ ውስጥ ተዘጋጅቶ የሚወጣና ለግንባታ ስራ የሚያገለግል ዱቄት።

ሲምፎኒ ስ በተለያዩ ብዙ የሙዚቃ መሳሪያዎች የሚቀነባበርና 3 ወይም 4 ክፍሎች የሚኖሩት የሙዚቃ ድርሰት።

ሲሪንጅ (ሲሪንጋ) ስ ቱቦ የሚመስልና ጫፉ ሹል የሆነ፥ በውስጡ ፈሳሽ መድሃኒትን ለመያዝና በደም ስር ለማስተላለፍ የሚያገለግል የህክምና መሳሪያ።

ሲሪንጅ

ሲራራ

ሲራራ ነጋዴ ስ የተለያዩ ሸቀጣ ሸቀጦችን በአጋሰስ፥... ጭኖ ከሃገር ወደ ሃገር እየሄደ የሚነግድ (ነጋዴ)።

ሲራክ^{1} ቅ ብልህ፥ አዋቂ።

ሲራክ^{2} ስ በወረቀትና በብራና ገፅ ላይ ፅሁፍ የሚያርፍበት ቦታ ወይም መስመር።

ሲር ስ ከተለፋ ቆዳ በቀጭኑ ተቀዶ የሚወጣ የከረቻ፥ የስልቻ ወይም ሌላ የቆዳ እቃ መስፊያ ወይም ከበሮ ማጅራት ላይ የሚሰጣ ጅማት።

ሲርሲርታ ስ 1. ሲር ሲር የሚል ድምፅ። 2. ከሳል ወይም ከ[illegible] የጉሮሮ ህመም የተነሳ የሚመጣ ሲር ሲር የሚል የአተነፋፈስ ሁኔታ።

ሲሳይ ስ 1. ምግብና መጠጥ፥ ሃብት የመሳሰለው ጠቀሜታ ያለው ነገር። 2. ጥሩ እድል።

ሲስተር ስ ሴት ነርሶች የሚጠሩበት ሙያን የሚያመለክት ስም።

ሲሶ ቅ ከሶስት አንድ እጅ ወይም አንድ ሶስተኛ።

ሲሶ አራሽ ስ ከተገኘው ምርት ከሶስት አንድ እጅ ለመስጠት በመዋዋል የሌላን ሰው መሬት የሚያርስ ገበሬ።

ሲቃ ስ ከመሮጥና ከመድከም፥ ከንዴት፥... የተነሳ የሚመጣ እንቅ እንቅ የሚያደርግ አተነፋፈስ።

ሲቃ ያዘው ከመሮጥ፥ ከመድከም፥ ከእልህ፥... የተነሳ ትንፋሹ እንቅ እንቅ አለ።

ሲቢጣ ቅ በጣም ቀጭንና አጭር የሆነ፥ ለአይን የማይሞላ (ሰው)።

ሲባጎ ስ 1. ቀጭንና ጠንካራ ገመድ። 2. (ዘይ.) ቀጭንና መጣጣ የሆነ (ሰው)።

ሲኒ (ስኒ) ስ ለቡና፥ ለሻይ፥... መጠጫ የሚያገለግል የሸክላ እቃ።

ሲኒ ማስቀመጫ ስ ሲኒን በላዩ ላይ ለማስቀመጥ ከሲኒው ጋር አብሮ የሚዘጋጅ ሰሃን መሰል እቃ።

ሲኒማ ስ በፊልም ተቀርፆ በፕሮጀክተር አማካይነት በኤሌትሪክ ሃይል እየተንፀባረቀ በነጭ ሰሌዳ ላይ የሚታይ የማንኛውም ነገር የሚንቀሳቀስ ምስል።

ሲኒማ ቤት ስ ህዝብ እየተሰበሰበ ገንዘብ ከፍሎ ሲኒማ እንዲመለከትበት የተዘጋጀ አዳራሽ፥ ፊልም ቤትም ይባላል።

ሲናር ስ ከገብስ ጋር የሚበቅልና ገብስ የሚመስል አረም።

ሲኖዶስ ስ 1. ጳጳሳትና ካህናት ስለቤተክርስቲያን አገልግሎት፥ ህግና ስርአት ለመወያየትና ውሳኔ ለመስጠት የሚያደርጉት ስብሰባ ወይም ጉባኤ። ውሳኔውም ሲኖዶስ ይባላል። 2. እስከ መካከለኛው ዘመን የተደረጉትን የሲኖዶስ ውሳኔዎች ይዞ የሚገኝ መፅሃፍ።

ሲኦል ስ 1. ክፉ የሰሩ ሰዎች እስከ እለተ ምፅአት ይኖሩበታል የሚባል የስቃይና የመከራ ቦታ። 2. (ዘይ.) አስፈሪ፥ አስጨናቂ፥ መጥፎ ጨለማ፥... የሆነ።

ሲካካ [ዶሮ] ስ እንቁላል የምትጥልና የምታስካካ ዶሮ።

ሲውሲዋ ስ ከፍ ያለ የዶሮ ጫጩት።

ሲጋራ(ሲጃራ) ስ በስስ ወረቀት ተጠቅሉ የሚጨስ ደረቅ ትምባሆ።

ሲጋራ ያጨሳል/ ይጠጣል ሲጋራን በእሳት በመለኮስ ጪሱን ይምጋል።

ሲጋራ መተርኮሻ ስ የሲጋራን አመድ ለማራገፍና ቁራጩን ለመጣያ እንዲሆን ተብሎ የተዘጋጀ እቃ።

ሲጢጥ ኣለ ግ "*ሰጠጠ" ስር ተመ.

ሲጥ

ሲጥ ኣለ ግ 1.አይጥ እንደምታሰማው ያለ ጩሀት አሰማ። 2. ሞተ።

ሲጥ^{2}

ሳ የ "ሰ" ፊደል ራብእ ዘር።

ሳ___ "ስ–" ን ተመ.

–ሳ "–ስ" ን ተመ.

ሳህን (ሰሃን) ስ ከሸክላ ወይም ከቆርቆሮ ወይም ከፕላስቲክና ከመሳሰሉት የሚሰራ የምግብ ማቅረቢያ እቃ።

ሳለ^{1} ግ የአንድን ነገር መልክ፥ ቅርፅ ወይም አንድን አይነት ሃሳብ በስእል አሳየ፥ ምስሉን በወረቀት፥ በሸራ፥ በግድግዳ፥ በዘተ. ላይ ቀረፀ፥ አሰፈረ፥ ነደፈ።

ሰኣሊ ስ የስእል ባለሙያ።

ስእል ስ ለአይን እንዲታይ ተደርጎ በወረቀት፥ በሸራ፥ በግድግዳ ወዘተ. ላይ በእርሳስ፥ በብሩሽ ፥በብእር...የተሰራ፥ የተነደፈ ወይም ከጠጣር ነገር የተቀረፀ የአንድ ነገር ወይም ሃሳብ፥ መልክ፥ ቅርፅ፥ ምስል።

ስእል ሰራ ስእልን በወረቀት፥ በሸራ፥... ላይ ነደፈ፥ ሳለ።

ስእል አነሳ አንድን መልክ፥ ፎቶግራፍ፥... አስመስሎ ነደፈ፥ ሳለ።

ስእል የመሰለች እጅግ ቆንጆ፥ መልከ መልካም (ሴት)።

ሳለ^{2} ግ ሞረደ፥ አሾለ፥ አተባ፥ ስለት አወጣ።

መሳል ስ ለመሳያ፥ ለመሞረጃና ለስለት ማውጫ የሚያገለግል ሻካራ ድንጋይ፥ ለሆቴ።

ስል ቅ የተሳለ፥ የተሞረደ፥ ስለት ያለው።

ስለት ስ 1. የቢላዋ፥ የጎራዴ፥... አፍ ወይም የሚቆርጠው ወገን። 2. እንደቢላዋና ሰንጢ የመሳሰለ ለመቁረጥ የሚያገለግል መሳሪያ።

ስለት አወጣ 1. ስል አደረገ፥ አተባ፥ ሞረደ። 2. ስል ሆነ፥ ተባ።

ስለታም ቅ ስለት ያለው፥ በቀላሉ መቁረጥ የሚችል (ቢላዋ፥ ሰንጢ፥...)።

ሳለ^{3} ግ ከጉንፋን ወይም ከሌላ ሁኔታ የተነሳ ከጉሮሮ አየርን በሃይልና በተደጋጋሚነት አስወጣ፥ ኡሁ ኡሁ አለ።

ሳል ስ ከጉንፋን ወይም ከሌላ በሽታ የተነሳ ትክ ትክ የሚያደርግ፥ ኡሁ ኡሁ የሚያሰኝ ህመም።

ሳል ተከለበት ሳል ፈጠረበት፥ ሳል ያዘው።

አሳለ ግ ትክትክ አደረገ፥ ኡሁ ኡሁ አሰኘ፥ ሳለ። *ጉንፋኑ በጣም አሳለው።*

*ሳለ

ስእለት(ስለት) ስ ይህን ካደረክልኝ ይህን አደርግልሃለሁ በማለት ለአምላክ፥ ለመላእክት፥... የሚቀርብ ልመና፥ ብፅአት።

ስለቱ ደረሰ የለመነው፥ የጠየቀው ተሟላለት።

የስለት ልጅ በብፅአት፥ በልመና፥ በስለት የተወለደ ልጅ።

ተሳለ ግ ይህን ካደረክልኝ ይህን አደርግልሃለሁ በማለት ለአምላክ፥ ለመላእክት፥... ልመና፥ ብፅአት አቀረበ።

ሳለ (ካለ)

ሳለ አይሰጥ (ካለ አይሰጥ) ስ ስጋውን ከላዩ ላይ እንደ ልብ ለመጋጥ የማያመች የአከርካሪ አጥንት።

ሳሳ ስ ቀጥ ብሎ የረዘመና የሾለ ባለክርከራት ቀንድ ያለው ሳረበል የዱር እንስሳ (ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።

ሳሳይሽ ስ በፋብሪካ የተመረተ የማግ አይነት።

ሳሌ ስ ከጋን አነስ ከእንስራ ተለቅ የሚል የሸክላ እቃ።

ሳል "ሳለ^{3}" ስር ተመ.

ሳልሳ ስ በቆርቆሮ የታሸገ የቲማቲም ድልህ።

ሳልሳዊ "ሰለሰ" ስር "ሳልሳይ"ን ተመ.

ሳልሳይ "ሰለሰ" ስር ተመ.

ሳልስ ገ.ከ.

ሳልስት "ሰለሰ" ስር "ሰልስት" ን ተመ.

ሳልስትና "ሰለሰ" ስር ተመ.

ሳሎን ስ በዘመናዊ ቤት ውስጥ ለእንግዳ መቀበያ የተሰራ ክፍል።

ሳመ ግ ፍቅርን፥ ናፍቆትን፥ አክብሮትን፥ ሰላምታን ለመግለፅ ወይም ለመማፀን የሌላን አካል በከንፈሩ ነካ፥ ጨመጠመ።

ሳሙና ቅ 1. ከሞራና ከልዩ ልዩ ንጥረ ነገሮች የሚሰራ፥ ቆሻሻን ለማስለቀቅ የሚረዳ አረፋ የሚወጣው የገላ፥ የልብስና የሌላም እቃ ማጠቢያ። ቅ 2. ፈገግ ያለ (የበቅሉ መልክ)። 3. (ዘይ.) ሞላጫ፥ አታላይ።

ሳሙና መታ ሳሙና ቀባ፥ በሳሙና ፈገፈገ።

ሳማ ስ ቅጠሉ የሚለበልብ ጥቃቅን እሾህ ያለበትና በአንዳንድ አካባቢ እየተቀቀለ የሚበላ የእፅዋት አይነት።

ሳምቡሳ "ሳንቡሳ" ን ተመ.

ሳምባ " ሳንባ" ን ተመ.

ሳምንት ስ 1. የሰባት ተከታታይ ቀናት ጊዜ። 2. ከሰኞ ጀምሮ እስከ እሁድ የሰባት ቀናት ጊዜ። 3. ስምንተኛ ቀን።

ሳምንታዊ ቅ በየሳምንቱ የሚደረግ፥ የሚወጣ፥...።

ሳር ስ ለከብት ግጦሽና ለቤት ክዳን፥ ለጉዝጓዝ፥... የሚውል እንደ እንግጫ፥ ሰርዶ፥ ሙጃና ሰንበሌጥ የመሳሰለው ሁሉ።

ሳረበል ቅ ሳር የሚበላ (እንስሳ)።

ሳርቅጠሉ ሁሉም ነገር፥ ሁሉም ሰው።

ሳር ቤት ስ ብዙውን ጊዜ ግርግዳው ክብ ሆኖ የሚሰራ ጣሪያው በሳር የሚከደን ጎጆ።

ሳርያን ስ የኮት ቅድና አሰፋፍ አይነት።

ሳሳ^{1} ግ 1. ስስ ሆነ፥ ቀጠነ። 2. ተራራቀ (የዘር አዘራር ወይም የሰብል አበቃቀል)። 3. በመንቃቀል፥ በማለቅ፥ ለመመለጥ ደረሰ (ፀጉር)።

ሰስ ቅ 1. ውፍረት የሌለው፣ ደንዳና ያልሆነ፣ ቀጭን። 2. የተራራቀ (የቡቃያ አበቃቀል)።

አሳሳ ግ 1. ሰስ አደረገ። 2. አራራቀ (ዝሪትን)። 3. ፈለቀቀ፣ ጥጥፍሬውን በማውጣት አሳሰሰ (ጥጥን)።

ሳሳ^2 ግ 1. ሰሰተ፣ ተስገበገበ። 2. አዘነ፣ ራራ።

ስሱ ቅ 1. ንፉግ፣ ስግብግብ፣ ስስታም።2. አዛኝ፣ ሩህሩህ።

ስስት ስ ንፍገት።

ስስታም ቅ ንፉግ፣ ቀብቃባ።

አሳሳ ግ 1. አጓጓ፣ አስጎመጀ። 2. አሳዘነ።

ሳቀ ግ ፊቱን ፈገግ በማድረግና ድምፅ በማሰማት ደስታውን ገለፀ፣ ፈነደቀ፣ ተንከተከተ።

መሳቂያ ቅ ማፌዣ፣ ማላገጫ፣ ማሾፊያ።

ሳቂታ ቅ ሳቅ የሚያበዛ፣ ደስተኛ።

ሳቅ ስ ፈገግ በማለት፣ በመንከትከት፣...የሚገለፅ የደስታ፣ የመገረም፣...ስሜት።

በሳቅ ፈረሰ በጣም ሳቀ፣ ተንከተከተ።

ሳቁ መጣ ሊያስቀኝ ደረሰ።

በሳቅ ፈነዳ በጣም ሳቀ፣ተንከተከተ።

ተሳቀበት በተናገረው፣ ባደረገው ነገር አድማጩ ወይም ተመልካቹ መደሰቱን፣ መገረሙን በመሳቅ ገለፀለት።

ተሳቀበት ተፌዘበት፣ ተላገጠበት።

አሳቀ ግ 1. ሳቅ ፈጠረ፣ አንከተከተ። 2. (የምፀት አነጋገር) አስገረመ፣ አስደነቀ።

አስቂኝ ቅ 1. የሚያስቅ፣ የሚያንከተክት፣ ሳቅ የሚያስመጣ። 2. ቧልተኛ፣ ቀልደኛ።

አሳሳቀ ግ 1. አጫወተ፣ አዝናና። 2. አቀዘ፣ አታለለ።

ሳበ ግ 1. ጎተተ፣ ወደራሱ አስጠጋ። 2. እየጎተተ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ አጓጓዘ። 3. ስሜትን ያዘ፣ አማረ፣ ማረከ። 4. መጠጠ፣ ማገ። 5. ጠራ፣ አመጣ (ሰይጣንን)። 6. ወጠረ፣ ገተረ።

መሳቢያ ስ 1. እንደኮመዲና፣ ጠረጴዛ፣ ቁምሳጥን በመሳሰሉ እቃዎች ላይ የሚገጠም፣ እየተሳበ የሚወጣና እየተገፋ የሚገባ እጀታ ያለው የእቃ ማስቀመጫ ኪስ። 2. ለአረቄ ማውጫ የሚያገለግል በገመድ የተጠቀለለ ቀርቀሃ።

ሳቢዘር ስ (ሰዋ.) አኳኋንን ወይም አደራረግን የሚገልፁ ቃላት። አፃፃፍ፣ አካሄድ፣ አያያዝ፣... የመሳሰሉት ቃላት ቅርፅ ሳቢ ዘር ይባላል።

ሳቢያ ስ 1. ሰበብ፣ መነሻ ምክንያት። *በእሱ ሳቢያ መጣ።* 2. ቀናው አረቄ ከወጣ በኋላ ደገመኛ የሚወጣው የአረቄ ቅራሪ። 3. የክረምቱን ጊዜ ረዥም አድርጎ በተጨማሪ የሚዘንብ ዝናብ። *ዘንድሮ ሳቢያ ዝናብ አለ።*

ሰበት ስ 1. አንድን አካል ከላይ ወደታች የሚያመጣ፣ የሚስብ ሃይል። 2. ማግኔትነት ያለው ነገር ወይም አካል፣ ብረትን ወይም ሌላ አካልን የመጎተት ወይም የመሳብ ሃይል።

ተሳበ ግ 1. ቀስ እያለ እየተጎተተ ተጓዘ፣ ተጠጋ። 2. ተማረከ፣ ስሜቱ ተያዘ። 3. እየተወጠረ እንደ ፕላስቲክ ተለጠጠ። 4. እየተጎተተ ወይም እየተንሰራፋ ሄደ፣ረዘመ (የሃረግነት ፀባይ ያለው እንደ ዱባ፣ ቅል ያለ ተክል)።

ተሳቢ ስ 1. የተሻጋሪ ግስ ድርጊት የሚያርፍበት ወይም የሚፈፀምበት ስም ወይም ተውላጠ ስም።"ተማሪው "መፅሃፉን አነበበ" በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ "መፅሃፍ" ተሳቢ ነው። 2. በመኪና ኋላ የሚቀጠል የእቃ ማጓጓዣ፣ ተጎታች።

ተሳሳበ ግ በዝምድና፣ በወዳጅነት፣...ተጠራሩ፣ ተገናኙ፣ ተደጋገፈ።

ሳቢሳ ስ ብዙ እየሆነ ከከብት ጋር ወንዝ ዳርና ውሃማ በሆነ ቦታ ላይ የሚሰማራ፣ መልኩ ነጭ፣ ቅልጥሙ ዘለግ ያለ አሞራ (ስእሉን አሞራ ስር ተመ.)።

ሳቢያ "ሳበ" ስር ተመ.

ሳብእ ስ እንደ "ሆ"፣ "ሎ"፣ "ሞ"፣... ያሉና ከሳድስ ዘር ቀጥሎ የሚገኙ ሰባተኛዎቹ የፊደላት ዘሮች መጠሪያ ወይም የድምፅ ምልክት።

ሳተ ግ 1. አላማውን፣ ኢላማውን ሳይመታ፣ ሳያገኝ ቀረ። 2. ረሳ፣ ዘነጋ። 3. (ዘይ.) ከእርጅና፣ ከህመም የተነሳ ሽንትን፣ አይነ ምድርን መቆጣጠር አልቻል አለ። 4. ትክክለኛ አቅጣጫውን፣ መንገዱን፣ ቦታውን፣ አድራሻውን አጣ።5. ሃጢአት ሰራ።6. አእምሮውን፣ ራሱን፣...መቆጣጠር፣ ማወቅ፣ መግዛት፣... ተሳነው። *በደረሰበት አደጋ ህሊናውን ሳተ።*

ስህተት ስ 1. ትክክለኛ ያልሆነ ስራ፣ መልስ፣ ነገር፣...። 2. ጥፋት፣ እንከን።

ስህተቱን አረመ የተሳሳተውን አስተካከለ።

ስህተት ሰራ ተሳሳተ።

ስህተተኛ ቅ 1. ትክክለኛ ያልሆነ። 2. ጥፋተኛ፣ ሃጢአተኛ፣ በደለኛ።

ተሳተ ግ 1.ተረሳ፣ ተዘነጋ። 2. ታለፈ፣ ተዘለለ።

ተሳሳተ ግ 1. ትክክለኛ ያልሆነ መልስ ሰጠ ወይም ትክክለኛ ያልሆነ ስራ ሰራ። 2. ትክክለኛ አድራሻውን አጣ። 3. ተሳከረ፣ ተፋለሰ፣ ተዛነፈ። 4. ስህተተኛ ሆነ። 5. ሃጢአት፣ በደል፣ ጥፋት ሰራ።

አሳተ ግ ሃጢአት እንዲሰራ አደረገ።

አሳቻ ቅ 1.የሚያሳስት፣ አደናጋሪ (አቅጣጫ፣ ቦታ፣ መንገድ፣...)። 2. አይን የማይገባ፣ ለአይን የማይመስል። 3. ሰዋራ፣ ድብቅ (ቦታ)።

አሳሳተ ግ 1. ስህተት እንዲሰራ አደረገ፣ ገፋፋ፣ አደፋፈረ። 2. አባባ፣ አሳከረ። 3. አደናገረ፣ አጭበረበረ፣ አወናበደ። 4. ሃጢአት፣ ስህተት፣ በደል አሰራ ወይም እንዲሰራ አደረገ።

አሳሳች ቅ 1. የሚያሳስት፣ ሃጢአት፣ ክፉ ነገር እንዲሰራ የሚገፋፋ። 2. ትክክለኛ ያልሆነ ነገር እንዲሰራ የሚያደርግ፣ የሚገፋፋ። 3. ውስብስብ፣ ተመሳሳይ የሆነና ለመረዳት፣ አንዱን ከአንዱ ለመለየት፣ ለማስታወስ ወይም በትክክል ለመስራት የሚያስቸግር፣ የሚያደናግር። ስ 4. የንጉስ ልብስ ወይም የሙሽራ ልብስ የሚመስል በመልበስ ከንጉሱ ወይም ከሙሽራው ጎን በመቆም ትክክለኛው እንዳይታወቅ የሚያደናግር ሰው።

ሳተላይት ስ 1. በመሬትና ሌሎች ፕላኔቶች ዙሪያ የሚሽከረከር፣ ተፈጥሯዊ አካል። ጨረቃ በመባልም ይታወቃል። 2.በመሬትና በህዋ ውስጥ በሚገኙ አካላት ዙሪያ የሚሽከረከር፣ ለመገናኛ፣ ለምርምርና ለልዩ ልዩ አገልግሎት የሚውል ሰው ሰራሽ አካል።

ሳተርን ስ ከፀሃይ ጀምሮ ሲቆጠር በርቀት ስድስተኛ ተራ ላይ የሚገኝና በዙሪያው ቀለበቶች ያሉት፣ በፀሃይ ዙሪያ ከሚሽከረከሩት ፕላኔቶች አንዱ(በተጨማሪ ፕላኔትን ተመ.)።

ሳተነ ግ ፈጠነ፣ ተንቀዠቀዠ።

ሳተና(ሳታና) ቅ ፈጣን፣ ቀልጣፋ፣ ከተፎ፣ ቀዥቃዣ።

ሳታት "ሰእት" ስር **"ሰእታት"** ን ተመ.

ሳታና "ሳተነ" ስር **"ሳተና"** ን ተመ.

ሳንሱር ስ ፅሁፎች፣ ፊልሞች፣ ሙዚቃዎች፣... ለህዝብ ከመቅረባቸው በፊት በፖለቲካና በሞራል በኩል የሚያስከትሉት ችግር እንዳለ የሚደረግ ምርምራ፣ ቁጥጥር፤ ቁጥጥሩን የሚያደርገው ክፍልም ሳንሱር ይባላል።

ሳንሳ (ወሳንሳ) ስ 1. ለሁለት ወይም ከዚያ በላይ በአንድነት ሆነው በአጣና ወይም በቃሬዛ የሚሸከሙት ሸክም። 2. ለአንድ ሰው የሚከብድን ነገር (ህመምተኛን፣ ሬሳን፣...) ለሁለት ለማንሳትና በትከሻ ለማጓጓዝ የሚያስችል መሸከሚያ እንጨት፣ ቃሬዛ።

ሳንቃ^{1} ስ ለመዝጊያ፣ ለወለል ወይም ለሌላ የእንጨት ስራ እንዲሆን ከትልቅ ዛፍ በስሱ እየተሰነጠቀ ወይም እየተጠረበና እየተሳሳ የሚወጣ እንጨት።

ሳንቃ^{2} ስ ከብር፣ ከወርቅ፣... የሚሰራና በደረት በኩል የሚሆን የለምድ ወይም የካባ ማያያዣ።

ሳንቡሳ (ሳምቡሳ) ስ የቀርኛ ዱቄት ሊጥ ተዳመጦ ከበሰለ በኋላ በውስጡ ብዙውን ጊዜ የበሰለ ምስር ወይም ስጋ እየተደረገና በሶስት ማእዘን እየተጠቀለለ በዘይት ተጠብሶ የሚዘጋጅ ምግብ።

ሳንባ (ሳምባ) ስ በሰውና በእንስሳት ደረት ውስጥ የሚገኝ፣ አየር ለመሳብና ለማስወጣት የሚረዳ የመተንፈሻ አካል።



ሳንባ (ሳምባ)

ሳንባ ቀለም ስ የሳንባን መልክ የሚመስል ቀለም።

ሳንባ ነቀርሳ ስ ሳንባን የሚያቆስል ተላላፊ በሽታ።

ሳንባ አቃፊ ስ ሳንባን አቅፎ የሚይዝ የሰውነት ውስጣዊ አካል።

ሳንቲ ሜትር "ሴንቲ ሜትር" ን ተመ.

ሳንቲም ስ 1. በጥቅል ወይም በዝርዝር የሚገኝ የብር ክፍልፋይ (መቶ ሳንቲም አንድ ብር ይሆናል)። 2. ገንዘብ። *ሳንቲም የለኝም።*

ሳንቲም የለውም ምንም ገንዘብ የለውም።

ሳንካ (ሳንክ) ስ ጥፋት፣ እንከን።

ሳንዱቅ (ሰንዱቅ) ስ የልብስ፣ የእቃ ማስቀመጫ ሳጥን።

ሳንድዊች ስ ዳቦ ከሁለት ቦታ ላይ ተሰንጥቆ የተጠበሰ ስጋ ወይም እንቁላል ወይም ልዩ ልዩ አትክልቶች በውስጡ ተጨምረውበት የሚዘጋጅ የምግብ አይነት።

ሳንጃ ስ በጠመንጃ ጫፍ ላይ የሚሰካና ጫፉ ሹል የሆነ ስለታም ጩቤ።

ሳካ ስ እንከን፣ ጉድለት፣ ነውር፤ ሳንካ፣ ሳንክ።

ሳክስፎን ኢቶ አካባቢ ባለች ቀጭን ተውለብላቢ ብረት አማካይነት ለሚፈጠረው ድምፅ ልዩ ልዩ ቃና ለመስጠት የሚያስችሉ ቁልፎች ያሉት በትንፋሽ የሚሰራ የሙዚቃ መሳሪያ (ስእሉን ሙዚቃ መሳሪያ ስር ተመ.)።

ሳይንስ ስ 1. ንድፈ ሃሳቦች፣ ህጎች፣ መላምቶች፣... ተጨባጭ በሆነ መንገድ በምክንያታዊነት እየተረጋገጡ ስለ ተፈጥሮና ስለ ህብረተሰብ ጥናት የሚደረግበትና የሚከማችበት የእውቀት ዘርፍ።2. ስለተፈጥሮ ማስተዋልና ሙከራ የሚደረግበት የትምህርት፣ የእውቀት፣ የምርምር መስክ።

ሳይንሳዊ ቅ ትክክለኛ የሆነ፣ በሙከራ፣

በማስተዋል፥በምክንያታዊነት የተደገፈ የአጠናንና የምርምር መንገድን የተከተለ።

ኢሳይንሳዊ ቅ ሳይንሳዊ የሆነ መንገድን ያልተከተለ።

ሳይኮሎጂ ስ ስለ አእምሮ ሁኔታና ጠባይ የሚያጠና የትምህርት ዘርፍ፤ ስነ አእምሮ፥ ስነ ልቡና።

ሳጹላ ስ 1. በገጠር አካባቢ ልጃገረዶች መሃል ራሳቸው ላይ በክብ የሚላጩት አለሜጨት። 2. ላለማግባቷ ምልክት እንዲሆን መሃል ራሷ ላይ ፀጉሯን በክብ የተላጨች ልጃገረድ። 3. ልጃገረድ።

ሳድስ ስ እንደ ሀ፥ ል፥ ም፥ ... ያሉ በሃምስና በሳብእ መካከል የሚገኙ ስድስተኞዎቹ የፊደላት ዘሮች መጠሪያ ወይም የድምፅ ምልክት።

ሳገ ግ ሻጠ፥ ሰካ።

ሳጋ ስ ክፍተት ባላቸው በግድግዳ እንጨቶች መካከል የሚሰካ ወይም የሚሻጥ አጠር ያለ እንጨት፥...። 2. ለቤት ግድግዳ የሚሆን ፍልጥ።

ተሳገ ግ ተሻጠ፥ ተሰካ።

ሳጠራ ስ 1. ከሸንበቆ ወይም ከቀርከሃ የሚሰራ ምንጣፍ፤ አጥሩ። 2. ከሸንበቆ ወይም ከቀርከሃ የሚሰራ እንደ ወንበር፥ ጠረጴዛ፥ ሌማት፥... ያሉ እቃ።

ሳጥን ስ 1. ከእንጨት ወይም ከብረት ወይም ከሌላ ነገር የተበጀና ብዙውን ጊዜ አራት ማእዘንነት ያለው የልብስ፥ የእቃ፥... ማስቀመጫ፤ ሳንዱቅ። 2. በሳጥን መልክ ወይም ቅርፅ የተዘጋጀ ሌላ ማንኛውም ነገር። 3. በውስጡ እንዲሞላበት፥ ለተለያዩ ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጥበት ወይም ምልክት እንዲደረግበት በወረቀት ላይ የተዘጋጀና በአራት ማእዘን የተከበበ ወይም የታጠረ ክፍት ቦታ (□)።

ሳፋ ቅ 1.ሙሉ፥ ያልጎደለ።2. ያልተበረዘ፥ ያልተቀላቀለ።

ሳፋ ወተት ስ ከሻይ ወይም ከቡና ጋር ያልተደባለቀ ንፁህ የፈላ ወተት።

ሳፋ ስ ለልብስ ማጠቢያ የሚያገለግል ሰፊና ጎድጓዳ የሆነ የቆርቆሮ ሳህን።

ሴ የ "ሰ" ፊደል ሃምስ ዘር።

ሴል ስ ህይወት ባላቸው አካላት ውስጥ የሚገኝ፡ ከህይወት ክፍልፋዮች ውስጥ የመጨረሻው ትንሹ ክፍል የሆነና ያለ ማጉያ መነፅር የማይታይ ህዋስ።

ሴሚናር ስ በተወሰኑ ርእሶች ላይ የጥናት ፅሁፎችን በማቅረብ ከተሳታፊዎቹ ጋር ውይይት ለማካሄድ ወይም በተወሰነ ጉዳይ ላይ ማብራሪያ፥ ገለፃ ለማድረግ የሚደረግ ስብሰባ።

ሴረኛ "*ሰየረ" ስር ተመ.

ሴራ ዝ.ከ.

ሴሰነ ግ አመነዘረ፡ ሸረሞጠ።

ሴሰኛ ቅ አመንዝራ፥ ሸርሙጣ፥ ቅንዝረኛ።

ሴት ስ 1. እንስት፤ ከወንዱ የተለዩ የተፈጥሮ ምልክቶችና ባህርያት ያሏት ሰው። 2. የልጃገረድነት ወጓን የጨረሰች ወይም ድንግልና የሌላት ሰው። ቅ 3. የተፈጥሮ የእንስትነት ምልክቶችና ባህርያት ያሏት (እንስሳ፥ ወፍ፥...)። 4. (ዘይ.) ፈሪ።

ሴት ተወ የግብረ ስጋ ግንኙነት አቆመ።

ከሴት ደረሰ የግብረ ስጋ ግንኙነት ፈፀመ (ወንድ)።

ሴተኛጤ ስ ያለባል ብቻዋን የምትኖር ሴት።

ሴታሴት ወንድ ሆኖ የሴትነት ጠባይ የሚታይበትና መሽቆርቆርና መኳኳል የሚያበዛ።

ሴት አኩሪ ስ እንደ ነባ ለዳቦ መጋገሪያነት የሚያገለግልና ቅጠሉ መጠነኛ ስፋት ያለው አነስተኛ የተክል አይነት።

ሴት አውል ስ ብዙውን ጊዜ ከሴቶች ጋር መሆን ወይም መዋል የሚወድ (ወንድ)።

ሴት አያት ስ የአባት ወይም የእናት እናት።

የሴቶች ገና ስ ከገና በፊት ያለው ቀን ወይም የገና ዋዜማ።

ሴተኛ አዳሪ ስ በሽርሙጥና የምትተዳደር ሴት፥ ሸርሙጣ ።

ሴቴ ቅ የታዋ ሴት የሆነ (እፅ፥ ተክል፥...)።

ሴቴ ዘር ስ ከወንዴው ዘር ጋር ተዋህዶ ፅንስ ለማፍራት የሚችል ከሴቷ የሚገኘው ዘር።

ሴትነት ስ የሴት ሙያ ወይም ባልትና።

ሴንቲሜትር (ሳንቲ ሜትር) ስ የርዝመት መለኪያ። 100 ሴንቲ ሜትር 1 ሜትር ይሆናል።

ሴንቲ ግሬድ ስ የሙቀት ወይም የቅዝቃዜ መጠን መለኪያ። 100⁰ ሴንቲ ግሬድ 212⁰ ፋራናይት ይሆናል።

ሴንጢ "ሰንጢ" ን ተመ.

ሴኮንድ "ሰኮንድ" ን ተመ.

ሴደር ስ ያቀይና የነጭ መቀነትማ ምልክት ያለው የከብት መልክ።

ስ የ "ሰ" ፊደል ሳድስ ዘር።

ስ ከ "ይ" ድምፅ በፊት ሲገባ "ሲ-"፥ ከ"አ" ድምፅ በፊት ሲገባ "ሳ" ይሆናል። በግስ ላይ በስተመነሻ እየገባ ግስን ከማስር የሚያስቀር ምእላድ። *ስፈልግ/ ሲ—ግ/ ሳያልፍ፡*

ስ 1. ጥያቄን ለማስከተል በተፈለገ ጊዜ በቃል መጨረሻ የሚገባ ምእላድ።"-ሳ"ም ይሆናል። *እርሳሱን ላገኘሁት፥ መፅሃፉሲሰጠኝ ምን አደርጋለሁ፡* 2. እፍራሽን ወይም የአወዳደሪ ሃሳብን

በሚያስከትሉ ቃላት መጨረሻ የሚገባ ምእላድ። *መስማትስ ትሰማላችሁ ግን ልብ አታደርጉም /ዝግጅትስ የበሬቱ ይበልጣል።*

ስሃ "ስሃ" ን ተመ.

ስህተተኛ "ሳተ" ስር ተመ.

ስህተት ዝ.ክ.

ስለ— 1. ቀዋሉ ወይም ተከትሉ "ለተጠቀሰው ነገር፥ ሃሳብ ሲባል" ለማለት የሚገባ ምእላድ። *ስለ እግዚአብሔር ብለህ ኢታስቸግር።* (ብዙውን ጊዜ ከግስ ወይም ከስም ጋር እየተባመረ የሚነገር)። 2. ቀዋሉ ወይም ተከትሉ "የተጠቀሰውን ቃል ወይም ርእስ" በሚመለከት የሚገባ ምእላድ። *ስለሃይማኖት ብዙ ተነጋገሩና/ስለመፅሃፉ ጉዳይ በእኔ ጣለው።* 3. ምክንያትን ለመግለጽ ወይም ለማመልከት የሚገባ ምእላድ። *መኪና ስለተበላሸ ዛሬ ልንሄድ አንችልም።* 4."እንደ" ለማለት የሚገባ። *ይህ የማሽላ እንጀራ እንዴት ጥሩ ነው፣ ስለ ጤፍ ይቆጠራል።* 5. በአንድ ነገር ወይም በሰው ምትክ መደረጉን ለማመልከት የሚያገለግል። *ስለእኛ ሞተ።*

ስለምን ተው.ግ. በምን ምክንያት፥ በምን መልክ፥ ለምን።

ስለዚህ መ.ተ. 1. ይህንን በሚመለከት፥ በዚህ ርእስ። *ስለዚህ ጉዳይ ከዚህ በፊት ተወያይተናል።* 2. በዚህ ምክንያት። *ሰዓቱ ደርሷል፤ ስለዚህ መሄድ አለብኝ።*

ስለላ "ሰለለ^{2}" ስር ተመ.

ስለታም "ሳለ^{2}" ስር ተመ.

ስለት^{1} ዝ.ክ.

ስለት^{2} "ሳለ" ስር "ስእለት" ን ተመ.

ስለስ "ሰለሰ" ስር ተመ.

ስሉጥ ቅ ስልጡን፥ ከተሜ።

ስላሴ "ሰለሰ" ስር ተመ.

ስላቅ "*ሰለቀ" ስር ተመ.

ስላች ስ ቀጭን፥ አቋራጭ መንገድ።

ስሌት "*ሰላ" ስር ተመ.

ስል^{1} "ሰላ^{1}" ስር ተመ.

ስል^{2} "ሰላ^{3}" ስር ተመ.

ስል^{3} "ሳለ^{2}" ስር ተመ.

ስልል

ስልል አይገባውም ዘወር ያለ አነጋገር አይገባውም።

ስልምልም "ሰለመ^{2}" ስር ተመ.

ስልሳ(ስድሳ) ስ 1. በሃምሳ ዘጠኝና በስልሳ አንድ መካከል ያለ ቁጥር መጠሪያ። በአሃዝ ሲፃፍ ፷ ፥ 60 ነው። ቅ 2. የስድስት አስሮች ድምር የሆነ።

ስልስ ስ በቲማቲምና በሽንኩርት የሚሰራ እንደ ወጥ ያለ ማባያ።

ስልቅ "ሰለቀ" ስር ተመ.

ስልባቦት ስ ከፈላ ወተት አናት ላይ የሚጋገር የወተት ቅባት።

ስልብ "ሰለበ" ስር ተመ.

ስልት ስ 1. ዘዴ፥ ብልሃት፥ መንገድ (የአሰራር፥ የነገር፥...)። 2. ምት (የሙዚቃ፥ የዳንስ፥...)። 3. ክፍል፥ አይነት፥ ወገን። *ኢቃውን በስልት በስልቱ አስቀመጠ።*

ስልተ ምርት ስ አንድ ህብረተሰብ ምርት የሚያመርትበትና የተመረተውንም የሚከፋፈልበት መንገድ ወይም ስርአት።

ስልቹ "ሰለቸ" ስር ተመ.

ስልቻ ስ ከፍየል ወይም ከበግ፥... ቆዳ ተለፍቶ የሚዘጋጅ ከረጢት፤ አቁማዳ።

ስልክ ስ ሩቅ ለሩቅ ያሉ ሰዎች ድምፃቸውን በሽቦ ወይም በአየር በማስተላለፍ የሚነጋገሩበት የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያ፤ ቴሌፎንም ይባላል።

ስልክ ደወለ በስልክ አማካይነት ከሚፈልገው ሰው፥ ድርጅት፥...ጋር መገናኘት የሚያስችል ጥሪ አደረገ።

ስልክ ቁጥር ስ ለእያንዳንዱ ስልክ መስመር የሚሰጥ የጥሪ መለያ ቁጥር።

ስልክ እንጨት ስ የስልክ ሽቦ ወይም መስመር የተዘረጋበት ረጅም ምሰሶ።

የስልክ መስመር ስ የስልክ መገናኛ።

የስልክ ማውጫ ስ የስልክ ደንበኞችን ስም፥ አድራሻና የስልክ ቁጥራቸውን የያዘ መዝገብ።

የስልክ ጥሪ ስ በስልክ አማካይነት የሚደረግ ግንኙነት።

ስልከኛ ስ የስልክ ጥሪዎችን የሚቀበልና የሚያገናኝ ወይም መልእክት የሚያስተላልፍ ሰራተኛ።

ስልክልክ "*ሰለከለከ" ስር "ስለከላካ" ን ተመ.

ስልጆ ስ ከባቄላ ዱቄትና ከሰናፍጭ የሚዘጋጅ እንደ ወጥ ያለ ማባያ።

ስልጡን "ሰለጠነ" ስር ተመ.

ስልጣኔ ዝ.ክ.

ስልጣን ዝ.ክ.

ስመኛ "ስም" ስር ተመ.

ስሙኒ ስ የብር አንድ አራተኛ፤ ሃያ አምስት ሳንቲም።

ስሚ "ሰማ^{1}" ስር ተመ.

ስሚንቶ "ሲሚንቶ" ን ተመ.

ስሚዛ ስ ግንዱ አንጓ ያለውና በቀላሉ ሊሰበር የሚችል፡ ቅጠሉ ሰፋ ሰፋ ያለ የእፅዋት አይነት፤ ሰንሰል።

ስማርድ ስ የአውሬ ወጥመድ።

ስማ በለው "ሰማ¹" ስር ተመ.

ስሜታዊ "ሰማ¹" ስር ተመ.

ስሜት ዝ.ክ.

ስም ስ 1. ለማንኛውም ሰው፥ ነገር፥ ቦታ፥... የሚሰጥ መጠሪያ። 2.(ሰዋ.) ለግሱ እንደ ባለቤት ወይም ተሳቢ ሆኖ ሊያገለግል የሚችል የሰው፡ የቦታ፡ የነገር፥ መጠሪያ ቃል። 3. አንድ ሰው ወይም ድርጅት የሚታወቅበት ስራ፥ ተግባር፥...። *በመስሪያ ቤቱ ውስጥ ጥሩ ስም የለውም።*

ለስሙ 1. ለይስሙላ ያህል፥ ለወሬው ያህል። *ለስሙ የሃብታም ቤት ነው እንጂ ግን ጥሩ ኑሮ አይኖሩም።* 2. ለክብር፥ ለዝና ሲባል። *ለስሟ መጠሪያ ቆና ሰፋች።*

በ__ ስም 1. __ን ሽፋን በማድረግ። *በሀዝብ ስም ማጭበርበር አይገባም።* 2. ስለ ። *በእግዚአብሄር ስም የተባረክ ይሁን።* 3. ን በመወከል። *በስራ አስኪያጁ ስም ገንዘቡን ያንቀሳቅሳል።* 4. ለ__ እንዲሆን፡ ለ__ ተብሎ። *በእርዳታ ስም ብዙ እህል ተላከ።*

ስሙ ጠፋ በክፉ ተነሳ፥ ተጠራ።

ስም ሰበረ የሰውን ስም አጠፋ፡ አጎደፈ፡ በመጥፎ አነሳ።

ስም ሰጠ 1. በመጥፎ አነሳ፡ ስም አጠፋ፡ አማ። 2. ሰየመ፥ መጠሪያ አወጣ። 3. አፃፈ፥ አስመዘገበ (ስሙን)።

ስም ተከለ በየጊዜው ስሙ እንዲጠራ፥ እንዲታወስ አደረገ(ብዙውን ጊዜ በጥሩ ስራ)።

ስም አስጠራ 1. ታዋቂ፥ ዝነኛ እንዲሆን አደረገ፥ አስመሰገነ። 2. የሟችን የክርስትና ስም በማውሳትና በማስጠራት አስቀረበ፥ አስቀደሰ፥ ዘከረ።

ስም አወጣ ሰየመ፥ መጠሪያ ሰጠ።

ስም አጠፋ የሰውን ታሪክ ወይም ዝና በመጥፎ አነሳ፥ አጎደፈ፥ ያልሆነውን ሆነ በማለት አወራ፥ አማ።

ስም አጥፊ ቅ የሰውን ታሪክ፥ ዝና፥... በመጥፎ የሚያነሳ፥ የሚያጎድፍ፥ ሃሜተኛ።

ስም ጠራ 1. የተመዘገበ የስም ዝርዝር ጠራ። 2. በፀሎት ላይ የሟችን የክርስትና ስም አነሳ።

ስመጥር (ስመጥሩ) ቅ የታወቀ፥ ዝነኛ (በጀግንነቱ፥ በሃብቱ ወይም በሌላ ስራው)።

ስም አይጠሬ ስ ስሙን በግልፅ መጥራት መጥፎ ነው ተብሎ የሚታመንበትን እንደ እባብ፡ ጉንዳን፥ አባጨጓሬ፥... ያለን ነገር ለመጥራት የሚያገለግል ተለዋጭ ስም። *ስም አይጠሬ መጣ።*

ስም ጠሪ ስ የሰዎችን የስም ዝርዝር ይዞ ስም በመጥራት፡ ያለውንና የሌለውን ሰው የሚቆጣጠር (ሰው)።

የስም መጥሪያ ስ የስም ዝርዝር ያለበት መዝገብ ወይም ወረቀት።

ስሙኛ ቅ ስም አጥፊ፥ ሃሜተኛ።

ስምሙ "ሰማ¹" ስር ተመ.

ስምም ዝ.ክ.

ስምምነት ዝ.ክ.

ስምረት "ሰመረ" ስር ተመ.

ስምሪት "*ሰማራ" ስር ተመ.

ስምንት ስ 1. በሰባትና በዘጠኝ መካከል ያለ ቁጥር። በአሃዝ ሲፃፍ ፰ ፥ 8 ነው። ቅ 2. ብዛቱ ሁለት አራቶችን የሆነ።

ስምንተኛው ሺህ ስ ክፋትና ተንኮል የሚበዛበት የአለም መጨረሻ ወይም የምፅአት ጊዜ ይሆናል ተብሎ የሚታመንበት ዘመን።

ስምጥ "ሰመጠ" ስር ተመ.

ስሞተኛ "ሰማ¹" ስር ተመ.

ስሞታ ዝ.ክ.

ስረ "ስር¹" ስር ተመ.

ስሬት "ሰራ²" ስር ተመ.

ስሬያ "ሰረረ" ስር ተመ.

ስራ "ሰራ¹" ስር ተመ.

ስራይ ስ 1. በሰው ላይ ጉዳት የሚያደርስ መድሃኒት ወይም መርዝ። 2. እንደ ጨጓራ በሽታ ያለ የሆድ ውስጥ ህመም፡ ደዌ።

ስር¹ ስ 1. ማንኛውም እፅዋት ምግቡን ከአፈር ውስጥ የሚወስድበትና ከመሬት ወለል በታች የሚውለው የተክሉ አካል። 2. በሰው፥ በእንስሳትና በአእዋፍ አካል ውስጥ የደም ማመላለሻ ሆኖ የሚያገለግል ቀጫጭን ጅማት። 3. ታችኛ ስፍራ። 4. መነሻ፥ መጀመሪያ፥ መሰረት። *ነገር ከስሩ ውሃ ከጥሩ።* 5. አጠገብ። *ከስሬ አይጠፋም።*

በ__ ስር መዋ. 1. በ _ በታች። 2. በ ውስጥ። *በጭቆና ስር ይማቅቃሉ።*

ከ__ ስር መዋ. ከ _ በታች።

ስር ሰደደ 1. ፀደቀ፥ ስሩ ወደታች ረዘመ፡ ጠለቀ። 2. ተደላደለ፥ መሰረት ያዘ፥ ፀና።

ስር ያዘ 1. መሰረት ያዘ። 2. ስር ሰደደ፡ ፀደቀ (ተክል)።

ከስር ከመነሻ፣ ከመሰረት፣ ከመጀመሪያ።

ስረ መሰረት ስ መነሻ፣ መጀመሪያ (የሃሳብ፣ የነገር፣...)።

ስረ ነገር ስ የነገር መነሻ።

ስረ ወጥ ቅ ቅጥያ የሌለውና አንድ ወጥ ሆኖ የተሰራ።

ስረ ብዙ ስ ስሩ ለጉንፋንና ለሳል መድሃኒት ይሆናል የሚባል እንስተኛ የሆነ የእፅዋት አይነት።

ስራስር ስ 1. እንደ ድንች የመሳሰሉና በምግብነት የሚያገለግሉ፣ ወፍራም ስር (ፍሬ) ያላቸው የተክል አይነቶች። 2. ለመድሃኒትነት የሚያገለግል የእፅዋት ስር።

ስር ሚዜ ስ አንደኛ ሚዜ።

ስር ማሽ ስ የስራስር መድሃኒት አዋቂ፣ ጠንቋይ፣ መድሃኒተኛ፣ መተተኛ።

ስርነቀል ቅ ከስር ከመሰረቱ ከፍተኛ ለውጥ የሚያመጣ።

ስርነቀል ለውጥ ስ በአንድ ነገር ላይ የሚታይ ፈጣንና መሰረታዊ የሆነ የአይነት ለውጥ።

ስርኩል ስ ተፈጭቶ የሚዘጋጅ የኩል አይነት።

ስር ጠምዛዥ ስ መተተኛ፣ በአስማት ወይም በመተት ሰው ይገላል የሚባል።

የስር ፍርድ ቤት ስ አንድን ጉዳይ ከይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በፊት በመጀመሪያ የተመለከተው ፍርድ ቤት።

ስርቻ ስ የማይታይ፣ ስዋራ፣ ደባቃ ቦታ።

ስር^2 "ሰራ^1" ስር ተመ.

ስር^3 "ሰራ^2" ስር ተመ.

ስርቅ

ስርቅታ (ስቅታ) ስ 1. ለመተንፈሻነት የሚያገለግለው ጡንቻና (ዲያፍራም) የአየር ቧንቧ እየተደጋገመ ሲኮማተር የሚፈጠር፣ ጉሮሮን እንቅ እያደረገ የሚወጣ ድምፅ፣ ሁቅታ። 2. የመጨረሻ የህይወት ትንፋሽ።

ስርቅ (ስቅ) አለው ሁቅ አለው፣ ስርቅታ ያዘው።

ስርአት ስ 1. አንድ ነገር የሚሰራበት ወይም የሚከናወንበት ደንብ፣ ህግ። 2. ወግ፣ ባህል።

ስርአት *ያዘ* ተስተካከለ፣ ጥሩ መልክ ያዘ።

ስርአተ ማህበር ስ በተወሰነ የእድገት ደረጃ የሚገኝ ህብረተሰብ ስልተ ምርትና ማህበራዊ ግንኙነት የተመሰረተበት ሁኔታ፣ የማህበረሰቡ የአመራረት፣ የአኗኗርና የአመለካከት ዘይቤ መሰረት።

ስርአተ ቀብር ስ በቀብር ጊዜ የሚከናወን ስነስርአት።

ስርአተ ትምህርት ስ ለትምህርት አሳማኝ ግብ መምታት በእቅድ እየተዘጋጀ በት/ቤቶች በየደረጃው የሚሰጥ አጠቃላይ የትምህርት ይዘት።

ስርአተ ንግስ ስ ታቦት ወይም ንጉስ በሚነግስ ጊዜ የሚደረግ ፀሎትና ስነ ስርአት።

ስርአት አልበኛ ቅ 1. የመንግስትን፣ የደንብንና የስነ ስርአትን መኖር የሚቃረን ወይም የሚቃወም። 2. በጥባጭ፣ አዋኪ።

ስርቅታ "ስርቅ" ስር ተመ.

ስርቆሽ "ሰረቀ^1" ስር ተመ.

ስርቻ "ስር^1" ስር ተመ.

ስርወ

ስርወ መንግስት ስ በዘር ግንድ ላይ የተመሰረተ ተከታታይነት ያለው የንግስና ሃረግ።

ስርወ ቃል ስ ለሌላው መነሻ የሚሆን ወይም ሌላ ምእላድ የሚቀጠልበት መሰረታዊ ወይም መነሻ ቃል።

ስርዋፅ ስ 1. እንደማስረጃ ሆኖ በነገር መካከል የሚገባ ተጨማሪ ቃል። 2. ሽብልቅ፣ ውሻል።

ስርዝ "ሰረዘ" ስር ተመ.

ስርየት "*ሰረየ" ስር ተመ.

ስርንጉጥ ቅ ወጣ ገባ የሆነ (ቦታ)።

ስርጥ "ሰርጥ" ን ተመ.

ስርጭት "*ሰረጨ" ስር ተመ.

ስሱ "ሳሳ^2" ስር ተመ.

ስስ "ሳሳ^1" ስር ተመ.

ስስታም "ሳሳ^2" ስር ተመ.

ስስት ዝ.ከ.

ስቃይ "*ሰቀየ" ስር ተመ.

ስቅለት "ሰቀለ" ስር ተመ.

ስቅሳት ዝ.ከ.

ስቅታ "ስርቅ" ስር "ስርቅታ" ን ተመ.

ስበበኛ "*ሰበበ" ስር "ሰበበኛ" ን ተመ.

ስበብ "*ሰበበ" ስር "ሰበብ" ን ተመ.

ስበት "ሳበ" ስር ተመ.

ስባሪ "ሰበረ" ስር ተመ.

ስባት "ሰባ" ስር ተመ.

ስብ ዝ.ከ.

ስብራት "ሰበረ" ስር ተመ.

ስብርባሪ ዝ.ከ.

ስብሰባ "ሰበሰበ" ስር ተመ.

ስብሳብ "ሰበሰበ" ስር "ሰበሰብ" ን ተመ.

ስብስብ "ሰበሰበ" ስር ተመ.

ስብሰብ "ሰበሰበ$_{2}$" ስር "ስብሰባ"ን ተመ.

ስብቀት "ሰበቀ^{2}" ስር ተመ.

ስብቅል^{1} ቅ ያማረ፥ የተዋበ::

ስብቅል^{2} "*ሰበቀለ" ስር ተመ.

ስብከት "ሰበከ" ስር ተመ.

ስብድብድ "*ሰበደበደ" ስር "ሰበድባዳ"ን ተመ.

ስብጥር "ሰበጠረ" ስር ተመ.

ስቱኮ (እስቱኮ) ስ 1. የበር ወይም የመስኮት መስታወት እንዳይንገጫገጭ መስተዋቱ በገባበት ስንጥቅ ውስጥ የሚጠቀጠቅ እንደ ሞቃ ያለ ማጣበቂያ:: 2. ከቀለም ቅብ በፊት ስንጥቃትን ለመድፈንና ቀለም እንዲቀበል ለማድረግ ግርግዳ ላይ የሚቀባ ኖራ መሰል ነገር::

ስቴንስል ስ በሰም ላይ ፅሁፍ ከተቀረፀበት በኋላ የተቀረፀውን ፅሁፍ በማባዣ መኪና አማካይነት በሌላ ወረቀት ላይ በተፈለገው ብዛት እያተሙ ለማውጣት የሚያስችል ልዩ የወረቀት አይነት::

ስቴዲዮም(እስታዲዮም) ስ ተመልካቾችንና ተወዳዳሪዎችን እንዲይዝ ተደርጎ የተከለለ፣ የተለያዩ ስፖርታዊ ክንውኖች (ብዙውን ጊዜ እግር ኳስ ጨዋታ) የሚካሄድበት ቅጥረ ግቢ፣ ሜዳ፤ ካምቦሎጆም ይባላል::

ስቴፕለር(እስቴፕለር) ስ የስቴፕለር መርፌ በውስጡ ተጨምሮበት ወረቀትን ለማያያዝ ወይም ለመስፋት የሚያገለግል መሳሪያ (ስእሉን የፅህፈት መሳሪያ ስር ተመ.)::

ስቴፕለር መርፌ ስ በስቴፕለር ውስጥ ተጨምሮ ወረቀት ለማያያዝ ወይም ለመስፊያ የሚያገለግል ሽቦ (ስእሉን የፅህፈት መሳሪያ ስር ተመ.)::

ስነ— 1. ውበትን የሚያመለክትና ከቃል በስተመነሻ ላይ የሚቀጠል ተጣማሪ ምእላድ:: *ስነ ግጥም*:: 2. ጥናት፥ ሳይንስ የሚለውን ለማመልከት ከቃል በስተመነሻ ላይ የሚቀጠል ተጣማሪ ምእላድ:: *ስነልሳን፥ ስነልቦና*...::

ስነልሳን ስ ቋንቋን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ የሚያጠና የእውቀት ዘርፍ::

ስነልቦና ስ 1. የአንድ ህዝብ የአስተሳሰብ ሁኔታ:: 2. የአእምሮን፥ የአስተሳሰብን፥ የሰውን ባህርይ ሁኔታ የሚያጠና ሳይንስ፤ ስነ አእምሮም (ሳይኮሎጂ) ይባላል::

ስነልቦናዊ ዘይቤ ስ አንድ ህዝብ ወይም ህብረተሰብ ከአኗኗሩ፥ ከልምዱ የተነሳ በአእምሮው ውስጥ ያለው ስሜት፥ አስተሳሰብ፥ አመለካከት::

ስነ መለኮት ስ የአምላክን ባህርይና ተግባራት የሚያጠና የሃይማኖታዊ ትምህርት ዘርፍ፤ ትምህርተ መለኮት::

ስነ ምግባር ስ 1. መልካም ጠባይ ወይም አድራጎት:: 2. በአንድ የሙያ መስክ ከባለሙያው የሚጠበቅ መልካም አድራጎት ወይም አሰራር:: 3. መልካምም ሆነ መጥፎ ባህርይ ወይም አድራጎት::

ስነ ስርአት ስ 1. ዲሲፕሊን፥ ስነ ምግባር:: 2. ደንብ፤ ህግ:: 3. አንድን ድርጊት በተመለከተ የተለመደ ስርአትን ወይም ደንብን ተከትሎ የሚካሄድ ክንውን::

ስነ ስቅለት ስ የክርስቶስን ስቅለት የሚያሳይ ስእል ወይም ቅርፅ::

ስነቃል ስ እንደ ተረት፥ እንቆቅልሽ፥ ምሳሌያዊ አነጋገር፥ የሰርግ፥ የለቅሶ ግጥም፥... ያለ ከትውልድ ወደትውልድ በቃል የሚተላለፍ አፋዊ ስነፅሁፍ፤ ኪነ ቃልም (ኪነተ ቃልም) ይባላል::

ስነአእምሮ የ "ስነልቦና" ን ሁለተኛ ፍቺ ተመ.

ስነውበት ስ ስለውበት ምንነት፥ አመጣጥ፥ እድገት፥ ህግና ሚና በማጥናት ስለኪነጥበብ አጠቃላይ ግንዛቤ የሚሰጥ የፍልስፍና ዘርፍ ::

ስነጥበብ ስ ስእልን፥ ቅርፃ ቅርፅን፥ ሙዚቃንና ስነ ፅሁፍን የመሳሰሉ ውበትን የሚያሳዩ የፈጠራ ስራዎች ሙያ::

ስነፅሁፍ ስ 1.በልብ ወለድ ወይም በግጥም መልክ የሚዘጋጅና ህይወትን ውብ በሆነ መልክ የሚያንፀባርቅ የፈጠራ ስራ:: 2. በአንድ ሃገር ውስጥ ባሉ ቋንቋዎች ተፅፎ የሚገኝ ማናቸውም የፅሁፍ ስራ::

ስነፈለክ ስ ስለከዋክብት ሁኔታና በልዩ ልዩ ነገሮች ባህርይ ወይም እጣ ላይ ስለሚያሳድሩት ተፅእኖ የሚያጠና የሳይንስ ዘርፍ::

ስነፍጥረት ስ 1. በምድርም ሆነ በሰማይ ላይ ያሉ ፍጥረታት በሙሉ:: 2. በአለም ላይ ስላሉት ፍጥረታት የሚያጠና ሳይንስ::

ስኒ "ሲኒ" ን ተመ.

ስናር በቅሎ ስ ፈጣንና ሰጋር የሆነ ረዥም በቅሎ (ከሱዳን ይመጣ የነበረ)::

ስናግ "ሰነገ^{1}" ስር ተመ.

ስንቀን ስ የተፈጨ ወይም የተደቆሰ ትንባሆ፥ ሱረት::

ስንቅ "ሰነቀ" ስር ተመ.

ስንቆ ስ እንደ ጎመን ያለና ተቀቅሎ የሚበላ የቅጠል አይነት::

ስንቡል ስ ጥሩ መአዛ ያለው የሽቶ አይነት::

ስንባጭ "ሰነበጠ" ስር ተመ.

ስንብት "ሰነበተ" ስር ተመ.

ስንት ቅ ቁጥርን፣ መጠንን፣ ብዛትን መጠየቂያ ቃል (ምን ያህል? ማለት ነው)።

ስንትና ስንት ብዙ። *ስራዎቹ ስንትና ስንት ናቸው።*

ስንተኛ ቅ 1. የአንድን ነገር የጥራቱን ወይም የአመጣጡን ቅደም ተከተል ወይም ያለውን ደረጃ ለማወቅ የመጠየቂያ ቃል። *በትምህርትህ ስንተኛ ወጣህ/ ስንተኛ ደረጃ ሆና ነው።* 2. ተራን፣ የድግግሞሽ ብዛትን መጠየቂያ ቃል። *ስንተኛ ነህ / እዚህ ስትመጣ ስንተኛህ ነው።*

ስንቴ(ስንትዬ) ስንት ጊዜ።

ስንትር "ሰነተረ" ስር ተመ.

ስንኝ "*ሰነኘ" ስር ተመ.

ስንኩል "ሰነከለ" ስር ተመ.

ስንክሳር ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) 1. የመላእክትን፣ የነቢያትን፣ የሃዋርያትን፣ የጻድቃንን፣ የሰማእታትን፣ የደናግልን፣ የመነኮሳትን፣ ወዘተ. የህይወት ታሪክ አጠናቅሮና አካቶ የያዘ ከአመት እስከ አመት የየእለቱን የገድል ታሪክ የሚናገር መጠነ ትልቅ የቤተ ክርስቲያን መፅሃፍ። 2. (ዘይ.) ሁ- ሃተታ የበዛበት፣ የተንዛዛ ነገር። ለ- ጣጣ። *ስንክሳርሽ በዛ።*

ስንኳን "እንኳን" ን ተመ.

ስንዝር "ሰነዘረ^{1}" ስር ተመ.

ስንደዶ ስ ለስፌት እቃና ለገመድ መስሪያ የሚያገለግል ረዘም ያለና ጠንካራ የሆነ የሳር አይነት።

ስንደዶ አፍንጫ ስ ቀጥ ያለና የተዋበ አፍንጫ።

ስንዱ "*ሰነዳ" ስር ተመ.

ስንዴ ስ ፍሬው ተቆልቶ፣ ተቀቅሎ የሚበላ ወይም ተፈጭቶ፣ ተቦክቶ ልዩ ልዩ የምግብ አይነቶችን ለማዘጋጀት የሚሆን የእህል አይነት።

ስንድቅ "ሰነደቀ" ስር ተመ.

ስንድድ ስ ሴቶች በእግራቸው ላይ የሚያደርጉት የጨሌ ጌጥ።

ስንግ^{1} ስ የእንግዴ ልጅ።

ስንግ^{2} "ሰነገ^{2}" ስር ተመ.

ስንጣሪ "ሰነጠረ" ስር ተመ.

ስንጣቂ "ሰነጠቀ" ስር ተመ.

ስንጥሬ ስ ፈሻምና ሹል መንቆር ያለውና ረግረጋማ በሆነ ቦታ የሚኖር የወፍ አይነት።

ስንጥር "ሰነጠረ" ስር ተመ.

ስንጥቅ "ሰነጠቀ" ስር ተመ.

ስንፍና "ሰነፈ" ስር ተመ.

ስእለት "*ሳለ" ስር ተመ.

ስእል "ሳለ^{1}" ስር ተመ.

ስካር "ሰከረ" ስር ተመ.

ስካቶላ ስ በተቦረቦረ ግድግዳ ውስጥ ገብቶ የሚጣበቅ የስልክ ወይም የኤሌክትሪክ ሶኬት አቃፊ።

ስኬታማ "ሰካ" ስር ተመ.

ስኬት ዝ.ክ.

ስክ ዝ.ክ.

ስክሪቢቶ (እስክሪብቶ) ስ ለመፃፊያ የሚሆን የጭቃ ቀለም ብእር።

ስኮላርሺፕ (እስኮላርሺፕ) ስ በመንግስት ወይም በሌላ ድርጅት እርዳታ አማካይነት የሚሰጥ የነፃ ትምህርት እድል።

ስኮላርሺፕ አገኘ ነፃ የከፍተኛ ትምህርት እድል ተሰጠው።

ስኮችቴፕ (እስኮች ቴፕ) ስ በአንድ በኩል ሙጫነት ያለው ከፕላስቲክ የሚሰራ ማጣበቂያ።

ስኳር ስ በሻይ፣ በኬክ፣...ውስጥ የሚገባ ከሸንኮራ አገዳ ወይም ከሌላ ነገር የሚሰራና ጣፋጭነት ያለው ነጭ የሆነ ደቃቅ ነገር።

ስኳር ድንች ስ ጣፋጭነት ያለው የድንች አይነት።

የስኳር በሽታ ስ በጣፊያ መታወክ ምክንያት በደም ውስጥ ከሚፈለገው በላይ ወይም ተመጣጣኝ ያልሆነ ስኳር እንዲገኝ የሚያደርግ በሽታ።

ስውር "ሰወረ" ስር ተመ.

ስያሜ "ሰየመ" ስር ተመ.

ስደተኛ "ሰደደ" ስር ተመ.

ስደት ዝ.ከ.

ስድ ዝ.ከ.

ስድሳ "ስልሳ" ን ተመ.

ስድስት ስ 1. በአምስትና በሰባት መካከል ያለ ቁጥር መጠሪያ። በአሃዝ ሲፃፍ ፮፣ 6 ነው። ቅ 2. ብዛቱ ሁለት ሶስቶችን የሆነ። *ስድስት ቤቶች።*

ስድስቶ(ስድስቶሽ) ስ በአንድነት እጅብ ብለው በሰማይ ላይ የሚታዩ የስድስት ከዋክብት መጠሪያ።

ስድብ "ሰደበ" ስር ተመ.

ስጉ "ሰጋ" ስር ተመ.

ስጋ ስ 1. የሰውን፣ የእንስሳትን፣ የአእዋፍን፣... አጥንት ሸፍኖ ከቆዳ በታች የሚገኘው ስብና

ጡንቻ ቅልቅል ያለበት ገላ። 2. ለምግብነት የሚያገለግል የእንስሳ ስጋ፤ ብልት። *የበሬ ሲጋ/የበግ ሲጋ።* 3. ዘመድ፡ ወገን።

ስጋ ሆነ ሰው ሆኖ ታየ ወይም ተገለጠ፣ የሰውን ባህርይ ያዘ (ክርስቶስ)።

ስጋ ለበሰ 1. ዝ.ከ። 2. በስጋ ተሸፈነ (እሾህ)።

ስጋ ለባሲ ቅ ስጋ የለበሰ (ሰው)።

ስጋዋን ሸጠች ሸረሞጠች (ገንዘብ ለማግኘት)።

ስጋ ያዘ ወፈረ፡ ደለበ (ከብቱ)።

የ ___ ን ስጋ እውነትነትን ለማረጋገጥ የሚደረግ መሃላ (የአባቴን ስጋ፣ የእናቴን ስጋ እንደማለት)።

ስጋ መብላት ማማት። *በሆነ ባልሆነው የሰው ስጋ መብላት ይወዳል።*

ስጋ በል ቅ ስጋ ብቻ የሚመገቡ እንስሳት (እንደ አንበሳ፣ ነብር ያሉ)።

ስጋ ቤት ስ 1. የስጋ ክፍል ሹም። 2. ስጋ የሚሸጥበት ቤት፤ ልኳንዳም ይባላል።

ስጋ ወደሙ ስ በሁብስትና በወይን መልክ የሚቀርብ የኢየሱስ ክርስቶስ ስጋና ደም፤ ቁርባን፤ መስዋእት።

ስጋ ወደሙ ተቀበለ ቆረበ።

ስጋደዌ (ደዌስጋ) ስ የቆምጥና በሽታ።

የስጋ ትል ስ ባልተዘለዘለና በቂ አየር ባላገኘ ወይም የሚደርቅበት አመቺ ሁኔታ ባልተፈጠረለት ስጋ ላይ የሚፈጠር ትል።

የስጋ ዘመድ ስ በደም ወይም በትውልድ የሚገናኙት ዘመድ።

ስጋዊ ቅ አለማዊ፤ መንፈሳዊ ያልሆነ።

ስግነት ዝምድና።

ስጋት "ስጋ" ስር ተመ.

ስጋዊ "ስጋ" ስር ተመ.

ስጋጃ ስ ከእንስሳት ፀጉር ወይም ከቃጫ ወይም ከክር፣... የሚሰራ ምንጣፍ።

ስግስግ "ሰገሰገ" ስር ተመ.

ስግብግብ "*ሰገበገበ" ስር ተመ.

ስግነት "ስጋ" ስር ተመ.

ስግደት "ሰገደ" ስር ተመ.

ስጎ(ሱጎ) ስ ለፓስታ፣ ለማካሮኒ፣... ማባያ የሚሆንና ከቲማቲም፣ ከስጋ፣...እና ሌሎች ማጣፈጫዎች የሚዘጋጅ የወጥ አይነት።

ስጥ "*ሰጣ" ስር ተመ.

ስጦታ "ሰጠ" ስር ተመ.

ስፋት "ሰፋ^{2}" ስር ተመ.

ስፌት "ሰፋ^{1}" ስር ተመ.

ስፍራ "ሰፈረ^{2}" ስር ተመ.

ስፒል(እስፒል) ስ ምስማር መሰል የወረቀት ማያያዣ ቀጭን መርፌ።

ስፓጌቲ(እስፓጌቲ) ስ ፓስታ።

ስፖርት ስ እንደ ዳማና ቼዝ የመሳሰለ የቤት ውስጥ ውድድር እንዲሁም የሰውነትን ቅልጥፍና የሚጠይቅ እንደ እግር ኳስ፣ ሜዳ ቴኒስ ያለ ጨዋታ ወይም የአካል ማጠንከሪያ እንቅስቃሴ።

ስፖርት ይሰራል የስፖርት እንቅስቃሴ ያካሂዳል።

ስፖርት ሜዳ ስ ስፖርት የሚሰራበት ቦታ።

የስፖርት ማዘውተሪያ [ስፍራ] ስ ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች የሚካሄዱበት ቦታ።

ስፖርተኛ ቅ በስፖርት ግጥሚያ ወይም በአካል ማሰልጠኛ እንቅስቃሴ ተሳትፎ ያለው።

ስፖንዳ ስ የከረምቦላ መጫወቻ ጠረጴዛ።

ስፖንጅ ስ ናይለን መሰል ከሆነ ነገር በፋብሪካ የሚሰራና ውሃ የመምጠጥ ባህርይ ያለው፤ ለፍራሽ፣ ለመቀመጫ፣ ለእቃ ማጠቢያ፣... የሚሆን ለስላሳ ነገር፤ ስፍነግ።

ስፖንጅ ትራስ ስ ከስፖንጅ የተዘጋጀ ትራስ።

ስፖንጅ ፍራሽ ስ ከስፖንጅ የተዘጋጀ ፍራሽ።

ሶ የ "ስ" ፊደል ሳብእ ዘር።

***ሶለሶለ**

ሶልሷላ ቅ ጦልጧላ፤ ወዲያ ወዲህ የሚንቀዠቀዥ፣ ዘዋሪ።

ተንሶለሶለ ግ ተንጦለጦለ፣ ወዲያ ወዲህ ተንቀዠቀዠ፤ ተንከለከለ።

አንሶለሶለ ግ አንጦለጦለ፣ ወዲያ ወዲህ አንቀዠቀዠ፣ አንከለከለ።

ሶለግ(ሶሉግ) ስ ከቁመ ከፍ ብሎ የሚገኘውና ቀጠን ያለው የጅራፍ አካል ወይም ክፍል (በእሉን ጅራፍ ስር ተመ.)።

ሶለግ ውሻ ስ ቀጭንና ሽንጠ ረዥም የሆነ አዳኝ ውሻ።

ሶላት "ሰላት" ን ተመ.

ሶላቶ(ሰላቶ) ስ ኢጣሊያዊ ወታደር።

ሶልሷላ "*ሶለሶለ" ስር ተመ.

ሶሉግ "ሶለግ" ን ተመ.

***ሶመሶመ**

ሶምሶማ ስ 1. ርትሬታ፤ ከደንገላሳ በፊት ያለ

የፈረስ ሩጫ። 2. ዝግ ያለና ሰውነትን ለማሟሟቅ የሚደረግ ሩጫ።

አሰመሰመ ግ አረተረተ፣ ደንገላሳ ለመጋለብ አነበነበ።

ሶማያ ስ 1. የጦር እጀታ። 2. (ዘይ.) ቀጥ ብሎ መለል ያለ ቁመና ያለው (ሰው)።

ሶምሶማ "*ሰመሰመ" ስር ተመ.

ሶሞሊና ስ ለሙቅ፣ ለገንፎ፣ ለዳቦ፣ … የሚሆን ፋርኖ ዱቄት።

ሶሬን ቅ ቀይ (በሬ ወይም ላም)።

ሶሬኔ (ሶሬን) ስ መልኳ ቀይ የሆነ የቆቅ አይነት።

ሶራ ስ 1. ግምጃ ወይም ሱቲ። 2. የጥቁርና የነጭ ጠቃጠቆ ያለበት ከብት።

ሶራ ወፍ (ሶራት) ስ የጥቁርና የነጭ ዝንጉርጉር የሆነች አብረቅራቂ ወፍ።

ሶርዝ ስ መልኩ ጥቁር የሆነ ራሰ ትልቅ አሳ።

ሶስት ስ 1. በሁለትና በአራት መካከል ያለ ቁጥር መጠሪያ። በአሃዝ ሲፃፍ ፫፣3 ነው። ቅ 2. ብዛቱ በሁለት ላይ አንድን የሚጨምር። *ሶስት ልጆች።*

ሶስቶ (ሶስቶች) ስ በሰማይ ላይ መደዳውን በሰልፍ ሆነው የሚታዩ ሶስት ከዋክብት መጠሪያ።

ሶስትያ ቅ ከሶስት አንድ እጅ፣ ሲሶ።

ሶሻሊስት ቅ በሶሻሊዝም የሚያምንና የሚመራ፣ የሶሻሊዝም ተከታይ።

ሶሻሊዝም ስ 1. የማምረቻ መሳሪያዎች በህዝብ ቁጥጥር ስር የሚውሉበት ስርአተ ማህበር፣ ህብረተሰባዊነት። 2. በካርል ማርክስና በፍሬድሪክ ኢንግልስ የተቀመረ የላብ አደሩ መደብ ርእዮተ አለም።

ሶታ ቅ ለግላጋ፣ ወጣት፣ ጥሩ አቋም ያለው።

***ሶክሶክ**

ሶክሷካ ቅ ጠልጧላ፣ ወዲያ ወዲህ የሚል።

ሱክሱክ አለ ግ ጡል ጡል አለ።

አሶክሶክ ግ ሱክ ሱክ አለ።

ሶኬት ስ ለገሳግ ጡቶች መሰኪያ የሚሆኑ ቀዳዳዎች ያሉትና ከኮረንቲ ሽቦዎች ጋር የሚያያዝ የኤሌክትሪክ እቃ።

ሶክሷካ "*ሶክሶክ" ስር ተመ.

ሶፋ ስ ምቹ መቀመጫና ድጋፍ ያለው ወንበር፣ ፎቴ።

ሷ የ "ሰ" ፊደል ፍንፅቅ ዘር።

ሸ

ሸ ከ "ሰ" ፊደል ዘር ቀጥሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል (ግእዙ ሆሄ)።

ሸህ(ሼህ) ስ የቁርአን ትምህርት ያለው፥ የቁርአን ምሁር።

ሸሆና (ሸኮና፥ ሰኮና) ስ የእንስሳት እግር ወይም መርገጫ ፤ ኮቴ።

ሸለለ ግ 1. በዜማና በግጥም የሰራውን ጀብዱ እየጠቃቀሰ አቅራራ። 2. አጌጠ፥ ተሽቀረቀረ፥ ተሸሞነሞነ።

ሸለለበት ኮራበት፥ ዘነጠበት፣ተጀነነበት ።

ሸላይ ስ 1. የሚያቅራራ (ሰው)። ቅ 2.ውብ፥ ሽቅርቅር፥ ያማረ።

ሽለላ ስ 1.ቀረርቶ። 2. መጊያጊያጥ፥ መሽቀርቀር።

*ሸለለ

ሸለሊት ስ "እንሽላሊት"ን ተመ.

ሸለል አለ ግ ሸረር አለ፤ ፈጠን ብሎ ሄደ (እንደ እንሽላሊት፥ እባብ ያለ ተሳቢ እንስሳ)።

ተንሻለለ ግ ሸለል አለ።

ሸለመ ግ 1. አስጌጠ፥ አስቆነጀ፥ አስዋበ፥ አሸሞነሞነ። 2. ቅርፅ አወጣ፤ አዥጎረጎረ፥ ጌጥ አበጀ፥ (በቀለም፥ በቅርፅ ማውጫ ወይም በመንቀሻ መሳሪያ)።3. ለፈፀመው ስራ ማበረታቻ የገንዘብ፥ የቁሳቁስ፥...ሽልማት ሰጠ። 4. ሳይጎዳ በቀላሉ ለቀቀ (ኩፍኝ፥ ፈንጣጣ)።

ሽልም ቅ ጌጥ ወይም ንቅሳት ያለበት።

ሽልማት ስ 1. የገንዘብ፥ የቁሳቁስ፥...ስጦታ፥ ዳረጎት። 2. ጌጥ እንዲሆን ተብሎ የተሰራ እንደ ንቅሳት፥ ሽንትራት ያለ ነገር።

ሽልምልም ቅ ዝጉርጉር (ዥጉርጉር)።

ተሸለመ ግ 1. ሽልማት፤ ስጦታ ተሰጠው። 2. ተጌጠ፥ ተሸሞነሞነ፥ ቅርፅ ተበጀለት፥ ተዥጎረጎረ።

ተሸላሚ ቅ ለሽልማት የቀረበ ወይም ሽልማት ያገኘ።

ተሸላለመ ግ ተጊያጊያጠ፥ ተነቀሰ፥ ተሸሞነሞነ።

ሸለም ስ የዘንባባ፥ የከባ፥ የሙዝ ሙሽራ፤ ውልብልቢት።

ሸለምጥማጥ ስ 1.ረዥም ጅራት ያለውና በዛፍ ቅርንጫፍ ላይ፥ በተሀረበረ ግንድ ወይም በጥሻ ውስጥ የሚኖር ድመት የሚመስል የዱርአውሬ (ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)። 2. (ዘይ.፥ ስድብ) ጥቁር።

ሸለሸለ ግ 1. ሰነጠቀ፥ ሰነተረ፥ ገመሰ (እርሻን)። 2. በዝቶ የበቀለን አገዳ ነቀለ (በማረሻ)።

ተሸለሸለ ግ በማረሻ ተሰነጠቀ፤ ተሰነተረ፤ ተገመሰ።

ሸለሸል ስ በዱር የሚገኝ የደረቀ የከብት እበት፥ ኩበት።

ሸለቀቀ ግ 1. ሳጠ፥ ገሰፈፈ፥ ገፈፈ፤ ቀረፈ። 2. (ከኪስ፤ ከቦርሳ ብርን) መዘዘ፥ አወጣ።

ሽልቃቂ ስ ልጣጭ፥ ግልፋፊ።

ተሸለቀቀ ግ ተላጠ፤ ተገሰፈፈ፥ ተገፈፈ።

ሸለቆ ስ በሁለት ተራሮች ወይም ከፍተኛ ስፍራዎች መካከል የሚገኝ ረባዳ ወይም ጎርጓዳ ቦታ።

*ሸለበ

ሽልብታ ስ ቀላል እንቅልፍ።

ሸለብ አደረገ ግ ለትንሽ ጊዜ አንቀላፋ።

አሸለበ ግ 1. አንቀላፋ፥ ለትንሽ ጊዜ ተኛ። 2. (ዘይ.) ሞተ። *እንደተኛ በዚያው አሸለበ።*

ሸለተ ግ 1. ላጨ፤ መደመደ (ፀጉርን)። 2. ጠረበ፤ ላገ፥ ቀረፀ። 3.(ዘይ.) ሀ - አታለለ፥ አሳተ፥ ሸነገለ። ለ ሸረደደ፥ አሽሟጠጠ።

ተሸለተ ግ ተላጨ፥ ተመደመደ፤ ፀጉሩ ተነሳለት።

አሸለተ ግ ጻነ፥ አገገመ፤ አማረ (ታሞ የነበረ ሰው)።

ሸለገ^{1} ግ አሰበ፤ አሰላ፤ ለካ፥ ገመተ፥ መዘነ፥ መጠነ።

ሸለገ^{2} ግ ሆዱን ወደ ውስጥ አስጠጋ፤ አጣበቀ።

ሸለገ^{3} ግ አታለለ።

አሽልግ ቅ አታላይ።

ሸለፈት ስ 1. ልንቡጥ፥ ወሸላ። 2. ልጣጭ፤ ግልፋፊ።

ሸለፈታም ቅ (ስድብ) ያልተገረዘ (ወንድ)።

ሸለፈፈ ግ ገሰፈፈ፥ ሳጠ፤ ቀረፈ፥ ገፈፈ።

ሽልፋፊ ስ ግልፋፊ።

ተሸለፈፈ ግ ተገሰፈፈ፥ ተሳጠ፤ ተቀረፈ፤ ተገፈፈ።

ሸመለለ ግ ጠቀለለ፥ ሸበለለ።

ሸመሸመ ግ 1.ከረተፈ፥ ሸረከተ፥ በቀላሉ ፈጨ። 2. በብዛት ቃመ፥ በላ (ፈረስ፥ በቅሎ፥... እህልን)።

ሸመቀ ግ አደባ፥ ደፈጠ፤ ተደበቀ (አደጋ ለመጣል)።

ሽማቂ ስ የደፈጣ ተዋጊ።

ሽመቃ ስ የደፈጣ ውጊያ።

ሸምቅ ተዋጊ ስ የደፈጣ ተዋጊ።

ሸምቅ ውጊያ ስ በማድፈጥና አደጋ በመጣል የሚካሄድ የውጊያ ስልት።

አሸመቀ ግ አደባ፥ አደፈጠ፥ ሸመቀ።

ሸመቀቀ ግ 1. በሸምቀቆ አስተሳሰር ሳብ አድርጎና አጥብቆ አሰረ፤ አነቀ። 2. ጠምድዶ ያዘ፥ አከማተረ። *እግሩን ሸምቀቆ ይዞት ሳላስኬድ ላለው።*

ሸምቀቆ ስ 1. የከረጢት አፍ ማሰሪያ ጥብጣብ፥ ገመድ፥...። 2. ከጭራ፥ ከጠፍር፥... የተበጀ የወፍ፥ የአውሬ መያዣያ ወይም ማነቂያ ወጥመድ። 3. አንደኛውን ጫፍ ሳብ ሲያደርጉት እንደሚጠብቅ ወይም አንቅ አድርጎ እንደሚይዝ ሆኖ የታሰረ ወይም የተቋጠረ ገመድ።

ተሸመቀቀ ግ ተሰበሰበ፥ ተሸበሸበ፥ ተጨማደደ።

ተሸማቀቀ ግ አፈረ፥ ደነገጠ፥ ፈራ። *በጥገኝነት ስለሚኖር ሁሌ እንደተሸማቀቀ ነው።*

አሸማቀቀ ግ አስፈራ፥ አስደነገጠ፥ አስጨነቀ።

ሸመቃ **"ሸመቀ"** ስር ተመ.

ሸመተ ግ 1. ገዛ፥ ገበየ (ብዙውን ጊዜ እህልን)። 2. (ዘይ.) ያዘ፥ አተረፈ። *ጥንቃቄ ባለማድረጉ በሽታ ሸመተ።*

ሸመታ ስ ግዥ (ብዙውን ጊዜ የወር አስቤዛ)።

ሸማች ስ እህልን ለንግድ ሳይሆን ለምግብነት የሚገዛ በላተኛ።

ሸመተረ ግ ሸነቆጠ፥ ገረፈ።

ሸመታ **"ሸመተ"** ስር ተመ.

ሸመነ ግ ሸማ ሰራ።

ሸማኔ ስ እንደኩታ፥ የአገር ልብስ፥ ጃኖ የመሳሰሉትን የሚሰራ ጥበበኛ።

[የ]ሸማኔ መወርወሪያ የሚያህል (የን.አነ.) በጣም አጭር የሆነ (ሰው)።

[የ] ሸማኔ እቃ ስ የሸመና ስራ የሚከናወንባቸው እንደ መነ፥ መወርወሪያ የመሳሰሉት።

የሸማኔ ዘንግ ስ ሸማኔ የሚሰራውን ሸማ የሚለካበትና የተወሰነ መጠን ያለው የርዝመት መለኪያ።

የሸማኔ ጉድጓድ ስ ሸማኔ እግሩን አስገብቶ የሚሰራበት እመሬት ውስጥ ያለ ጉድጓድ።

***ሸመደመደ**

ሸመድማዳ (ሸምድምድ) ቅ ውልክፍክፍ፥ ጥምልምል፥ ልፍስፍስ፥ ለዋሳ።

ሸምድምድ አለ ግ ተሸመደመደ።

ተሸመደመደ ግ 1.ተልፈሰፈሰ፥ተጥመለመለ። 2. አቅም፥ ጥንካሬ አጣ (መንግስት፥ ኢኮኖሚ፥...)።

አሸመደመደ ግ 1. አጥመለመለ፥ አልፈሰፈሰ። 2. አቅም፥ ጥንካሬ አሳጣ፥ አዳከመ (መንግስትን፥ ኢኮኖሚን፥...)።

ሸመደደ ግ 1. ጨልጦ ጠጣ። 2. ቃል በቃል አጠና፥ በቃሉ ያዘ።

ሸምዳጅ ቅ ሁሉንም ቃል በቃል የሚያጠናና በቃሉ የሚይዝ።

ሸመድማዳ **"*ሸመደመደ"** ስር ተመ.

ሸመገለ ግ 1. አረጀ፥ በእድሜ ገፋ። 2. አስታረቀ፥ ገላገለ፥ አስማማ።

ሸምጋይ ስ አስታራቂ፥ አስማሚ።

ሽማግሌ ስ 1.በእድሜ የገፋ አዛውንት። 2. አስታራቂ፥ ገላጋይ።

ሽማግሌ ተላከበት የሚማልድ አስታራቂ፥ ጥያቄ የሚያቀርብ ሰው ወደ እርሱ ሄደ ወይም ተላከ።

ሽምግልና ስ 1. እርጅና። 2. የማስታረቅ፥ የማስማማት፥ የማማለድ ተግባር።

ሸመጠረ ግ ከመጠጠ።

ሸምጣራ ቅ ከምጣጣ።

ሸመጠጠ¹ ግ 1. ፥ ዝመገገ፥ መዝረፈን፥ ለቀመ(ፍሬን፥ እሸትን)። 2. ዥው አድርጎ ጠጣ፥ ጨለጠ። 3. በፍጥነት ሮጠ፥ ጋለበ። 4.(ዘይ.) ዋሸ፥ አበለ። 5. ገረፈ፥ ቆነደደ። 6. ወደ ኋላ አስተኛ (እንስሳ ጆሮውን)።

ሸምጥ ስ ፈጣን የፈረስ ግልቢያ።

ሸመጠጠ² ግ ተርታውን በተተከሉ ቋሚ የአጥር እንጨቶች ላይ እንደ ላጋም፥ ክትክታ፥ ቀጨሞ ያሉ ጨፈቃዎችን እያወሳሰበ ወይም እያጠላለፈ አጠረ።

ሸምጥ ቅ በጨፈቃ ተጠላልፎ ወይም ተወሳስቦ የታጠረ (አጥር)።

ሸሚዝ ስ ቀለልና ሳሳ ካለ የጨርቅ አይነት የሚሰራና እጅ ሙሉ ወይም ጉርድ ወይም ኮሌታ ያለው ወይም የሌለው፥ አብዛኛውን ጊዜ ወንዶች ከካኒተራ በላይ ከኮት ስር የሚለብሱት የልብስ አይነት።

ሸማ ስ እንደኩታ፥ ነጠላ፥ ጃኖ፥ ጋቢ ያለ ከድርና ከማግ የሚሰራ ልብስ።

ሸማሜ ስ ራሰ ትልቅ ሰንዴ።

ሸማቂ **"ሸመቀ"** ስር ተመ.

ሸማች **"ሸመተ"** ስር ተመ.

ሸማኔ **"ሸመነ"** ስር ተመ.

ሸማዳ ቅ ወል.ጋዳ፥ ወሸማዳ።

ሸምቀቆ **"ሸመቀቀ"** ስር ተመ.

ሸምቃቃ ዝ.ክ.

ሸምበቆ "ሸንበቆ" ን ተመ.

ሸምዳጅ "ሸመደደ" ስር ተመ.

ሸምጋይ "ሸመገለ" ስር ተመ.

ሸምጣራ "ሸመጠረ" ስር ተመ.

***ሸሞነሞነ**

ሽሙነሙን ቅ በአኳኋኑ ኩንስንስ፣ በአለባበሱ መጊያጊያጥ የሚያበዛ።

ሽሙንሙን አለ ግ ተሸሞነሞነ።

ተሸሞነሞነ ግ ተሽፋፈነ፣ ተከናነበ፣ ተኩነሰነሰ፣ አጌጠ፣ ተቆነጃጀ።

አሽሞነሞነ ግ አኩነሰነሰ፣ አስጌጠ፣ አሳመረ፣ አቆነጀ፣ አስዋበ።

***ሸሞጠጠ**

ሽሙጥ ስ የሽርደዳ፣ የአሽሙር፣ የአግቦ ንግግር።

ሽሙጥጧ ዝ.ክ.

አሽሟጠጠ ግ ሸረደደ፣ አንጓጠጠ፣ አሽሙር፣ አግቦ ተናገረ።

አሽሟጣጭ ቅ ሸርዳጅ።

ሸረሞጠ ግ አመነዘረ፣ ሴሰነ።

ሽርሙጣ ስ (ስድብ) 1. አመንዝራ። 2. ሴተኛ አዳሪ። 3.(ዘይ.) በባህርዩ አንዴ ከአንዱ ሌላ ጊዜ ከሌላው የሚሆንና ነገር የሚያወሳስብ ወረተኛ።

ሽርሙጥና ስ 1. አመንዝራነት። 2.ሴተኛ አዳሪነት። 3. (ዘይ.) በአንድ አቋም አለመርጋት፣ ከሁሉም ጋር አለሁ ማለት። *የፖለቲካ ሽርሙጥና።*

ተሽራሞጠ ግ 1. ሸረሞጠ፤ የብልግና ንግግር ተናገረ። 2. (ዘይ.) ጠባዩ መጥፎና ተለዋዋጭ ሆነ።

***ሸረረ**

ሽረር አለ ግ 1. ፈቀቅ፣ ዘወር አለ። 2. (በሽታ) ተወት አደረገ፤ ፋታ ሰጠ። 3. ተንሻሎ ሄደ። 4.ሿ ብሎ ወረደ፣ ፈሰሰ(ቀጭን ተቅማጥ)።

ሽረር አደረገ ግ እንደ ውሃ ያለ ተቅማጥ ተቀመጠ።

ተንሻረረ ግ ፈጥኖ አለፈ፣ ተንሻለለ፣ ተወረወረ፣ ሽር ብሎ ሄደ።

አንሻረረ ግ ወረወረ፣ አንሻለለ።

ሸረሪት ስ ትናንሽ ከሆኑና 8 እግር ካላቸው ፍጥረታት አንዷ የሆነችና በምግብነት የሚያገለግሏትን ነፍሳት ለማጥመጃ ድር የመሰለ ነገር የምታደራ ነፍሳት።

ሸረሪት

የሸረሪት ድር ስ ሸረሪት የምታደራው ድር።

ሸረሸረ ግ ቦረቦረ፣ ሰረሰረ፣ ፈለፈለ።

ሽረሽር ስ ፈረፈር፣ ፈፋ፣ ጉድባ፣ የተሸረሸረ ቦታ።

ተሸረሸረ ግ ተቦረቦረ፣ ተሰረሰረ፣ ቀስ በቀስ ተበላ፣ ተናደ።

***ሸረሸረ**

ሽርሽር ስ ለመዝናናት፣ ለመደሰት የሚደረግ ጉዞ።

ተሸራሸረ ግ 1. የተበላ ምግብ በቀላሉ በጨጓራ ተፈጨ። 2. ተሽጋሸጎ ተቀመጠ።

ተንሸረሸረ ግ ሰገረ፤ ፈጥኖ ተራመደ (በቅሎ)።

ተንሸራሸረ ግ ተዘዋወረ፤ ተናፈሰ፤ ለመዝናናት ወዲያና ወዲህ ሄደ።

አንሸረሸረ ግ አሰገረ (በቅሎን)።

አንሸራሸረ ግ 1. ለማዝናናት፣ ለማስደሰት፣ ወደ መንገድ ይዞ ሄደ፤ አናፈሰ፣ ነፋስ እንዲቀበል አደረገ። 2. የተበላ ምግብ በቀላሉ በጨጓራ እንዲፈጭ አደረገ (መጠጥ)። 3. አሽጋሸገ።

ሸረሸር "ሸረሸረ" ስር ተመ.

ሸረቆጠ ግ ቀልጠፍ፣ ሽንቀጥ አለ፤ ተሰበሰበ (በአለባበስ፣ በአካሄድ፣ በአቀማመጥ)።

ሽርቋጣ (ሽርቁጥ) ቅ ሽንቃጣ።

ሸረበ ግ 1. ሶስት ወይም አራት የሚሆኑ ገመዶችን፣ ክሮችን፣... በአንድነት ያበለ፣ እየደረበ ገመደ። 2. ሹርባ ሰራ፣ ጎነጎነ፤ አሸመ። 3. (ዘይ.) ነገርን፣ ሴራን አውጠነጠነ፣ ዶለተ።

ሹሩባ (ሹርባ) ስ የራስ ፀጉር ጉንጉን። (ስእሉን ፀጉር አሰራር ስር ተመ.)

ሹሩባ ሰሪ ስ የሴት ፀጉር የምትጎነጉን ወይም የምትቆነድድ ሴት።

ሹርቤ ብርሌ ስ አንገቱ ቀጭንና ረዥም የሆነ ሽልም ብርሌ(ስእሉን ብርሌ ስር ተመ.)።

ሽርበሽ ስ የተፈተለ ገመድ ወይም ጅራፍ።

***ሸረተተ**

ሸርተቴ(ሸተቴ) ስ 1. ቁልቁለት ወይም ተዳፋት ከሆነ ቦታ ላይ ሆነው ወደታች እየተንሸራተቱ የሚጫወቱት የልጆች ጨዋታ። 2. የተቅማጥ በሽታ።

ሸርታታ ቅ (ዘይ.) ወላዋይ፥ በቃሉ የማይረጋ።

ተንሸራተተ ግ 1. ወደታች እየተንፏቀቀ ወረደ፥ ተንሸተተ። 2. (ዘይ.) ወላወለ፤ ከዳ፤ በቃሉ ሳይረጋ ቀረ።

አንሸራተተ ግ አዳለጠ፥ አዳጠ፥ አንሸተተ።

አንሸራታች ቅ የሚያንሸራትት፤ የሚያዳልጥ (ቦታ)።

ሸረኛ "**ሸር**" ስር ተመ.

***ሸረከ**

ሸሪክ(ሸርካ፥ ሸርክ) ስ 1. በጋራ ወይም በአንድነት የሚሰራ ወይም የሚነግድ። 2. ወዳጅ፥ ባልንጀራ፤ ጓደኛ።

ሸርክና ስ 1. የህብረት ስራ ወይም ንግድ። 2. ወዳጅነት፤ ጓደኝነት።

ተሻረከ ግ ተባበረ፤ ተወዳጀ፥ ጓደኛ ሆነ፥ ተስማማ።

አሻረከ ግ አብሮት እንዲሰራ ወይም እንዲነግድ ተስማማ።

***ሸረከረከ**

ሸረክራካ (ሽርክርክ) ቅ ወላዋይ።

ተሸረከረከ ግ ተፍረከረከ፥ ወላወለ።

ሸረከተ ግ 1. ቀደደ፥ ተረተረ፥ ዘረከተ። 2. ሳያደቅ ፈጨ፥ ገረደፈ፥ ከካ። 3. (በጦር፥ በጩቤ) ወጋ፥ ዘነጠለ።

ሸርካታ ቅ (ዘይ.) ውሸታም።

ሸርከት ስ 1. ያልደቀቀ፤ ያልላመ (ዱቄት)። 2. (ዘይ.) ውሸታም።

ተሸረከተ ግ 1. ተቀደደ፥ ተተረተረ። 2. ሳይደቅ ተፈጨ፥ ተገረደፈ፤ ግርድፍ ሆነ። 3. (ዘይ.) ዋሽቶ ተናገረ፥ ዘባረቀ።

ሸረክራካ "***ሸረከረከ**" ስር ተመ.

ሸረደደ ግ 1. አሽሟጠጠ፥ አሾፈ፤ አላገጠ፥ ፎተተ። 2. ያልሆነውን ነገር እንዲህ ነው እያለና በውሸት እያጋነነ ተናገረ።

ሸርዳጅ ቅ አሽሟጣጭ፤ ፎታች።

ሸርደዳ ስ የአሽሙር፤ የሽሙጥ ንግግር።

***ሸረጠ**

ሸርጥ ስ 1. ከወገብ በታች የሚውል ግልድም። 2. ቆሻሻን ለመከላከል በልብስ ላይ የሚለበስ፤ የስራ ልብስ። 3. ለሃዘን ተብሎ ተዘቅዝቆየተለበሰ ነጠላ።

ተሸረጠ ግ (ክፉ፥ መጥፎ መንፈስ፥...) ለቀቅ አደረገ፥ ገለል አለ፤ ተወ።

ተሸረጠለት (ዛር፥ ቆጣ) ተወገደለት፤ ጠፋለት፥ ወደ ቀድሞው ጤናማ ሁኔታ ተመለሰ።

አሸረጠ ግ አገለደመ፥ አደገደገ።

አሸረጠች በሃዘን ጊዜ ነጠላዋን ዘቅዝቃ ለበሰች።

ሸረፈ ግ 1. በትንሹ ቆረሰ፥ ሰበረ። 2.(ከብት) ጥርሱን ነቀለ። 3. መነዘረ፤ ዘረዘረ፤ ወደ ቅንስናሽ ገንዘብ ለወጠ። 4. ቀነሰ፤ ቆነጠረ።

ሸራፋ ቅ 1. የተሰበረ (እቃ፥ ጥርስ፥...)። 2. (ስድብ) ጥርሱ የተሸረፈ። 3. በጣም አጭርና ክሳሳ የሆነ (ሰው)።

ሸርፍ ስ ምንዛሪ።

ሽራፊ ቅ ተሰብሮ፥ ተቆርሶ የወጣ ነገር፤ ስባሪ።

ሽርፍራፊ ቅ 1. ስብርባሪ። 2. ምንዛሪ፤ ቅንስናሽ ገንዘብ።

ተሸረፈ ግ ከላዩ ላይ ትንሽ ተቆረሰ ወይም ተሰበረ።

ተሸራረፈ ግ 1. ጫፍ ጫፉ ብዙ ቦታ ላይ ተሰበረ። 2. ከላዩ ላይ ተቀነሰለት።

አሸረፈ ግ (ገንዘብን) ዘረዘረ፤ መነዘረ።

ሸሪራ^{1} ስ 1. ኮርኒስ ላይ የሚመታ ቀጭን እንደ ማስመሪያ ያለ እንጨት። 2. ከመጋረጃ ጨርቅ ጋር ተያይዘው ወደ ግራና ቀኝ እየተንሸራተቱ መጋረጃውን መክፈትና መዝጋት የሚያስችሉት ባለ ሃዲድ ትናንሽ ቀለበቶች የሚንሸራተቱበት ጠፍጣፋ ባለሃዲድ ዘንግ ወይም ብረት።

ሸሪክ "***ሸረከ**" ስር ተመ.

ሸራ ስ ድንኳን፥ ቦርሳ፤ ሻንጣ፤...ለመስራት ወይም በላዩ ላይ ስእልን ለመስራት የሚያገለግል ጠንካራና ሻካራ የሆነ ጨርቅ።

ሸራ [ጫማ] ስ ከሸራ የሚዘጋጅ ጫማ።

ሸራፋ "**ሸረፈ**" ስር ተመ.

ሸር ስ ተንኮል፥ ክፋት፤ ደባ።

ሸር ሰራ ተንኮል፤ መጥፎ ድርጊት ፈፀመ።

ሸረኛ ቅ ተንኮለኛ፤ ክፉ፥ መሰሪ፥ ሴረኛ።

ሸርሙጣ "**ሸረሞጠ**" ስር ተመ.

ሸርተቴ "***ሸረተተ**" ስር ተመ.

ሸርታታ ዝ.ከ.

ሸርካታ "**ሸረከተ**" ስር ተመ.

ሸርዳጅ "**ሸረደደ**" ስር ተመ.

ሸርጣን ስ ብዙ እግር ያለው የባህር ነፍሳት፤ ጎርምጥ።

ሸርጣን

ሸርጣን [ውሃ] ስ በሰኔ ወር የሚወጣ የኮከብ አይነት። በተጨማሪም "**ኮከብ ቆጠራ**"ን ተመ.

ሸሸ ግ 1. ከፍርሃት የተነሳ ወደ ኋላ ተመልሶ ሮጠ፤ ፈረጠጠ። 2. ራቀ፣ ተለየ። *በገዛ ጥፋቱ ከጓደኞቹ ሸሸ።* 3. መገኘቱ ቀረ፤ ጠፋ። *ሃብት ሸሸው።* 4. (በሽታ፤ ነገር፤...) እንዳያጋጥመው፤ እንዳያገኘው ተጠነቀቀ። 5. ቦታውን ለቀቀ፤ ዘመመ፤...።

ሽሽት ስ ከአደጋ ወይም ከሌላ ነገር ለማምለጥ የሚደረግ እንቅስቃሴ፤ ስደት፤ ፍርጠጣ።

መሸሻ ስ መጠጊያ፤ መከለያ፤ መደበቂያ።

አሸሸ ግ 1. አገለለ፤ ሰወረ፤ ሸሸገ፤ ደበቀ። 2. አራቀ።

ሸሸገ ግ (እንዳይታይ፤ እንዳይታወቅ) ደበቀ፤ ሸፈነ፤ ከለለ፤ ጋረደ።

ሽሽግ ቅ ድብቅ፤ ስውር።

ተሸሸገ ግ ተደበቀ፤ ተሰወረ፤ ተከለለ።

ሸቀለ ግ ተሸከመ፤ የጉልበት ስራ ሰራ።

ሸቃይ ስ ተሸካሚ፤ ኩሊ።

ሽቀላ ስ የጉልበት ስራ (በአብዛኛው ሸክም)።

ሸቀሸቀ ግ 1. ሰቀሰቀ፤ መሳልሶ ወጋ። 2. ጠዘጠዘ፤ አመመ፤ ነዘነዘ (ህመም)።

አሸቀሸቀ ግ 1.ተንጠለጠለ፤ አዘበዘበ፤ ሊወድቅ ወይም ሊፈርስ ደረሰ። 2. በህመም ምክንያት ቆዳው ሊገፈፍ ወይም ሊቀረፍ ደረሰ፤ አፈከፈከ።

***ሸቀሸቀ**

ተንሸቀሸቀ ግ ፈራ፤ ራደ፤ ተንቀጠቀጠ።

አንሸቀሸቀ ግ አስፈራ፤ አራደ፤ አንቀጠቀጠ።

ሸቀበ ግ 1. (በሽያጭ ላይ) አታለለ፤ አሞኘ። 2. (የአራዳ እን.) ለከፈ፤ በነገር ነካ።

ሸቃባ ቅ (ስድብ) የሚሸቅብ፤ አታላይ፤ ገደቢስ።

ሸቀን ስ በሰውነት ላይ የተጋገረ እድፍ።

ሸቀናም ቅ (ስድብ) እድፋም፤ ጭቅቅታም፤ ቆሻሻ።

ሸቀጠ ግ ሸጠ፤ ለወጠ፤ ቸረቸረ፤ ነገደ።

ሸቀጥ ስ ለራስ ፍጆታ ሳይሆን ለትርፍ የሚሸጥና ጥቅም ላይ የሚውል ማንኛውም እቃ።

ሸቀጣሸቀጥ ስ በአይነት የተለያዩና ብዛት ያላቸው ለሽያጭ የሚቀርቡ እቃዎች።

ሸቃጭ ስ ቸርቻሪ ነጋዴ።

ሸቁራራ(ሸቆረር) ቅ አይነ አፋር።

ሸቃባ "ሸቀበ" ስር ተመ.

***ሸቆመቆመ**

ሽቁምቁም ቅ ግድርድር፤ አይነ አፋር።

ተሸቆመቆመ ግ ተግደረደረ።

ተሸቆምቋሚ ቅ ሽቁምቁም።

አሸቆመቆመ ግ አግደረደረ።

ሸቆረር "ሸቁራራ" ን ተመ.

***ሸቆጠቆጠ**^{1}

ሽቁጥቁጥ (ሽቆጥቋጣ) ቅ ደግ፤ ትሁት፤ ታዛዥ፤ ለሰው የሚጨነቅ ወይም የሚቸገር፤ ርግብግብ።

ተሸቆጠቆጠ ግ 1. አክብሮትን፤ ፍቅርን በማሳየት ታዛዥ ሆነ፤ ደግነትን፤ ትህትናን፤ አሳየ። 2. ተለማመጠ፤ ፈራ፤ ተርበደበደ።

አሸቆጠቆጠ ግ አስፈራ፤ አርበደበደ፤ አስጨነቀ።

***ሸቆጠቆጠ**^{2}

ተሸቆጠቆጠ ግ አጌጠ፤ ተዋበ፤ አማረ። *በወርቅ የተሸቆጠቆጠ ካባ ለብሷል።*

አሸቆጠቆጠ ግ አስጌጠ፤ አስዋበ።

ሸቆጥቋጣ"*ሸቆጠቆጠ^{1}"ስር **"ሽቁጥቁጥ"**ን ተመ.

ሸበለለ ግ ጠቀለለ።

ሽብልል (ሽብል) ቅ 1. ጥቅልል። ስ 2. ወፈር ተደርጎ የተዘጋጀ የገብስ ሊጥ።

ተሸበለለ ግ (ወረቀቱ፤ ብራናው) ተጠቀለለ።

ሸበለቀ ግ 1. ጫፉን አሾለ። 2. በጦር፤ በአንካሴ፤ በሽብልቅ ወጋ።

ሽብልቅ ስ ውሻል፤ ቅርቃር፤ ሹል እንጨት ወይም ብረት።

***ሸበለበለ**

ሽብልብል ቅ ሽፍንፍን፤ ጥቅልል።

ተሸበለበለ ግ 1. ተሸፋፈነ፤ ተጠቀለለ። 2. (ዘይ.) አማረ፤ ተሸሞነሞነ።

አሸበለበለ ግ 1. ሸፋፈነ፤ ጠቀለለ። 2. (ዘይ.) ሁ•አሳመረ፤ አሸሞነሞነ። ለ•አባበለ፤ አቆላመጠ፤ ተለማመጠ።

ሸበላ ስ 1. የእንስት፤ የኮባ፤...መሸረ። 2.

አቋቋሙ መልካም፥ ውብ፥ መዘዘ::

***ሸበረ**

ሽብር ስ ረብሻ፥ ሁከት፥ ብጥብጥ::

ሽብር ፈጣሪ ቅ 1. ረብሽ፥ አዋኪ፥ ሰላምን አደፍራሽ፥ በጥባጭ:: 2. (ድርጅት ወይም የድርጅት አባል) በመሳሪያ ሃይል አላማውን ለማስፈፀም የሚሞክር ሽብርተኛ::

ሽብርተኛ ቅ ሽብር ፈጣሪ::

ተሸበረ ግ 1. ተረበሸ፥ ታወከ፥ ተበጠበጠ፥ ፀጥታ ደፈረሰ:: 2. ፈራ፥ ደነገጠ፥ ባባ፥ ተጨነቀ::

ተሸባሪ ቅ በቀላሉ የሚደነግጥ፥ የሚረበሽ::

አሸበረ ግ 1. አወከ፥ በጠበጠ፥ ፀጥታ ነሳ:: 2. አስፈራ፥ አስጨነቀ::

አሸባሪ ቅ በጥባጭ፥ አዋኪ፥ ሰላምን አደፍራሽ::

***ሸበረቀ**

ሽብርቅ አለ ግ 1. አማረ፥ ተዋበ:: 2. አንፀባረቀ::

አሸበረቀ ግ አማረ፥ ተዋበ፥ አጌጠ::

አሸብራቂ ቅ ያማረ፥ የተዋበ፥ የሚያንፀባርቅ::

***ሸበረከ**

ሽብራካ ቅ ወልጋዳ፥ አሻሻ::

ሽብርክ አለ ግ 1. በርከክ አለ:: 2. (ዘይ.) እሺ አለ፥ ከቁጣው በረደ፥ ለሰለሰ አለ::

አሸበረከ ግ በርከክ አለ::

ሸበሸበ ግ 1. አጨማደደ፥ አኮማተረ:: 2. (ቀሚስን) ሸነሸነ::

ሽብሽብት ስ የቀሚስ ወገብጌ ወይም የእጅጌ ሽንሽን::

ሽብሽቦ ስ ሽንሽን ቀሚስ::

ተሸበሸበ ግ ተጨማደደ፥ ተኮማተረ::

***ሸበሸበ**

ሽብሽባ ስ 1. በመንፈሳዊ ዜማ የታጀበ ውዝዋዜ:: 2. ዘፈንን ለማድመቅ የሚደረግ ጭብጨባ፥ ጭፈራ፥ ውዝዋዜ::

አሸበሸበ ግ 1. በመንፈሳዊ ዜማ እየታጀበ አረገደ፥ ተወዛወዘ:: 2. በዘፈን እየታጀበ ጨፈረ፥ ተወዛወዘ፥ አጨበጨበ::

አሸብሻቢ ቅ በመንፈሳዊ ዜማ እየታጀበ የሚያረግድ፥ አስረጋጭ (ካህን)፥...:: 2. እያጨበጨበ፥ እየተወዛወዘ ዘፈንን የሚያዳምቅ:: 3. (ዘይ.) አጨብጫቢ፥ አሽቃባጭ::

ሸበበ ግ (በገመድ፥ በጠፍር) የበሬን፥ የበቅሎን አፍ አሰረ፥ ለጎመ::

መሸበቢያ ስ የበሬን፥ የበቅሎን አፍ ማሰሪያ፥ መለጎሚያ::

ሽብ አደረገ ግ ሳይጠብቅ ላላ አድርጎ አሰረ::

ተሸበበ ግ 1. ዝናብ፥ ብርድ እንዳይገባ የቤቱ ዙሪያ ተጋረደ::2. (አፉ) ተለጎመ፥ ታሰረ::

ሸበተ ግ 1. (አብዛኛውን ጊዜ ከእርጅና የተነሳ) ነጭ ፀጉር አወጣ:: 2. (ለእንጀራ፥ ለጠላ፥...) ሻገተ::

ሸበቶ ቅ 1. ነጭ ፀጉር ያወጣ:: 2. በእድሜ የገፋና ሽበት ያወጣ::

ሽበት ስ አብዛኛውን ጊዜ ከእድሜ መግፋት የተነሳ የሚወጣ ነጭ ፀጉር::

ሽበታም ቅ (ሰው) ሽበት ያወጣ::

ሸበድ ስ ከበገድ ግራና ቀኝ ያለ የጭንና የሆድ መጋጠሚያ ቦታ::

ሸበጥ ስ ነጠላ ጫማ::

ሽብራካ “*ሸበረከ” ስር ተመ.

ሸተ ግ 1. ጎመራ፥ ደረሰ፥ በሰለ:: 2.(ዘይ.) አማረ፥ ተዋበ::

እሸት ስ ለመበላት የደረሰ ሊጋ የእህል ዛላ፥ ዘለላ፥ እንቡጥ ፍሬ::

አሸተ ግ ጎመራ፥ ደረሰ፥ በሰለ፥ ፍሬ ያዘ::

ሸተተ ግ 1. ጠረኑ ወይም ሽታው ለአፍንጫ ተሰማ፥ አወደ:: 2. ገማ፥ ከረፋ፥ ቆነሰ::

ሽታ ስ 1. የአንድ ነገር ጠረን፥ መአዛ (ለአፍንጫ የሚሰማ):: 2. በተፈጥሮ ገላ ላይ የሚወጣ ጥቁር ምልክት::

ለሽታ ያህል በትንሹ ወይም በመጠኑ ለአመል ያህል::

ሽቶ (ሽቱ) ስ መልካም መአዛ ካላቸው እፅዋትና ዝባድ የተሰራ ጥሩ ሽታ ያለው ፈሳሽ::

ተሻተተ ግ ትንሽ ትንሽ ተዳረሰ (ምግብ፥ መጠጥ)::

አሸተተ ግ 1.የአንድን ነገር መአዛ ወይም ጠረን በአፍንጫ ማገ፥ ሳበ:: 2.እንዲገማ፥ እንዲከረፋ አደረገ:: *ስጋውን አሸተተከው::*

አሻተተ ግ ትንሽ ትንሽ አዳረሰ (ምግብ፥ መጠጥ)::

ሸቱቴ “*ሸረተተ” ስር **“ሽርትቴ”** ን ተመ.

ሸነሸነ ግ 1. ሸበሸበ፥ ሽንሽን እንዲሆን አደረገ:: 2. ከፋፈለ፥ ቆራረሰ:: 3. (እንጨትን) በቀጭኑ ሸነጣጠረ፥ ሰነጣጠቀ፥ ፈለጠ::

ሽንሽን ስ የተሸበሸበ ቀሚስ::

ተሸነሸነ ግ 1. ተሸበሸበ:: 2. ተከፋፈለ፥ በትንሽ በትንሹ ተዳረሰ::

ሸነቀረ ግ 1. ቀረቀረ፥ ሸጎጠ:: 2. (የሱሪን፥ የቀሚስን ጫፍ ውሃ ወይም ጭቃ እንዳይነካው)

ሰበሰበ፡ ቀነፈ፣ ከፍ አድርጎ ሻጠ።

ሽንቅር ቅ የተወተፈ፣ የተቃረቀረ።

ተሸነቀረ ግ ተቃረቀረ፣ ተሸጓጠ፡ ተወተፈ።

ሽነቀጠ ግ ቀልባሌ፡ ቀልጣፋ ሆኖ አማረ፡ ተዋበ።

ሽንቃጣ(ሽንቅጥ) ቅ ከወገቡ ቀጠን ያለ፡ ሸበላ።

ሽነቆረ ግ ቀደደ፡ ነደለ፣ በሳ።

ሽንቁር(ሽንቋራ) ቅ ብስ፣ ቀዳዳ።

ተሸነቆረ ግ ተቀደደ፣ ተነደለ፡ ተበሳ።

ሽነቆጠ ግ 1.በአርጩሜ፣ በአለንጋ፣... መታ፣ ሾጥ አደረገ፤ ገረፈ። 2. (ዘይ.) አሰቃየ፡ ጎዳ (ብርድ፡ ችግር...)።

አሸንቋጠ ስ መግረፊያ፡ አርጩሜ፡ አለንጋ።

ሽነተረ ግ በጣ፡ ቀደደ፡ ሰነጠጠ።

ሽንትር ቅ 1. የተሰነጠጠ፡ ብጥ። 2. እንደሰንበር ወይም እንደንቅሳት ያለ መስመር፣ ጌጥ፡ ሽልማት።

ሽንትራት ስ እንደሰንበር ወይም ንቅሳት ያለ መስመር ወይም ጌጥ።

ተሸነተረ ግ 1. ተበጣ፣ ተቀደደ። 2. ሰንበር ወይም መስመር አወጣ።

ሽነተፈ ግ በጣ፣ ቆረጠ።

ሽነከፈ ግ 1. የአህያን፣ የበግን፣...አንዱን የፊት እግር አጥፎ ወይም ከርትሞ አሰረ፡ ሰነከለ፡ ቀየደ። 2. በጣም ሳያጠብቅ ላላ አድርጎ አሰረ።

ሽንካፋ(ሽንክፍ) ቅ (ስድብ) እግሩ ወይም እጁ ሰንኩል የሆነ።

ሽነገለ ግ 1. ደለለ፣ አሞኘ፡ አታለለ። 2. አባበለ፣ ተለማመጠ፡ ለመነ። 3. አለከፈ፣ በመጠኑ አበላ።

መሸንገያ ስ ማባበያ፤ መደለያ፡ ማታለያ የሚሆን አነስተኛ ስጦታ።

ሽንጋይ ቅ አታላይ፡ ሰውን የሚያሞኝ።

ሽንገላ ስ ድለላ፡ ለማባበል ሲባል የሚነገር ወይም የሚደረግ ነገር።

ተሸነገለ ግ በትንሽ ነገር ተደለለ፤ እሺ አለ፡ መሸንገያ ተቀበለ።

*ሽነገረ

ሽንጋራ ቅ (ስድብ) ሸውራራ።

ውሽንግር ዝ.ከ.

ተሸናገረ ግ 1. ተንሸዋረረ፣ ተጠናገረ። 2.ተወላገደ፣ ተጣመመ።

አሸናገረ (አወሸናገረ) ግ 1. አይንን አንሸዋረረ። 2. አወላገደ፡ አጣመመ።

ሸነኘ ግ በጉባኤ ፡ በስብሰባ መከረ ወይም ዶለተ።

ሸንጎ ስ 1. ህዝብ የሚሰበሰብበት ወይም ዳኛ የሚያስችልበት ቦታ፣ አደባባይ። 2. ጉባኤ፣ ስብሰባ። 3. በሸንጎ ላይ የተሰበሰበ ህዝብ። 4. የሸንጎው ሰብሳቢ የሆኑት ሽማግሌዎች ወይም የጉባኤው የበላይ አካላት።

ሸንጎኛ ስ በሸንጎ ላይ እየተገኘ የሚከራከር፡ የሸንጎ ሰው።

ሸነጠ ግ የጀግንነትን ስሜት ወይም ወኔን ቀሰቀሰ (ቀረርቶው)።

*ሸነፈ

ሽንፈት ስ መረታት፡ ድል መሆን።

ተሸነፈ ግ 1. ድል ሆነ፡ ተረታ። 2. አቃተው፣ ደከመበት። 3. (ዘይ.) እንቢታውን ተወ፣ እሺ አለ፣ ተቀበለ።

ተሸናፊ ቅ በውድድር ወይም በጦርነት የተረታ።

አሸነፈ ግ 1. ድል መታ፣ ረታ። 2. አቃተ፣ አልቻል አለ። 3. እሺ አሰኘ፣ የተባለውን እንዲቀበል አደረገ።

አሸናፊ ቅ (በውድድር፡ በግጥሚያ፣...) ድል አድራጊ።

ሸና ግ 1. ሽንቱን ለቀቀ ወይም አፈሰሰ። 2. (ለምሳሌ ባትሪ ድንጋይ) ፈሳሽ ነገርን ከአካሉ ውስጥ አመነጨ፣ አወጣ፡ ርጥበት አሳየ።3. (ዘይ.) ፈራ።

ሽንት ስ ከሰውነት ውስጥ በብልት በኩል የሚወጣ ቆሻሻ ፈሳሽ።

ሽንትህን ይባርከው ዘርህን ይባርከው።

ሽንተ መልካም ጥሩ ዘር ያፈራ፡ ጥሩ ልጆች ያሉት።

ሽንት ማጥ ስ ሽንትን በቀላሉ ለመሽናት የሚከለክልና የሚያስምጥ ህመም።

ሽንት ቤት ስ መፀዳጃ ቤት።

የሽንት ቤት ወረቀት ስ ሽንት ቤት የሚሄድ ሰው በመፀዳጃ ጊዜ የሚገለገልበት ስስና ለስላሳ ወረቀት።

የሽንት ጨርቅ ስ ለህፃናት ሽንትና አይነ ምድር መቀበያ እንዲሆን ከወገብ በታች የሚጠቀለሉበትና በትንንሹ ተቆራርጦ የተዘጋጀ ጨርቅ።

ሽንታም ቅ 1. ሽንቱን በላዩ ላይ የሚለቅ። 2. (ዘይ.፣ ስድብ) ፈሪ፣ ቦቅቧቃ።

ሽንቋራ "**ሸነቆረ**" ስር "**ሽንቁር**" ን ተመ.

ሽንበቆ(ሸምበቆ) ስ መቃ።

የሸምበቆ ምርኩዝ የማያዋጣ፡ አምኖ የተጠጋውን ሊረዳ ወይም ሊደግፍ የማይችል።

ሽንተረር ስ ግራና ቀኝ ገደል ወይም ተዳፋት፣

የሆነና መካከሉ ከላይ እስከታች እንደሰንበር ሆኖ የሚወርድ የመሬት ቅርፅ።

ሽንከኛ "ሽንክ" ስር ተመ.

ሽንካፋ "ሽንከፈ" ስር ተመ.

ሽንኬሎ "ሰንኬሎ" ን ተመ.

ሽንክ ስ ተንኮል።

ሽንከኛ ቅ ተንኮለኛ።

ሽንኮራ [አገዳ] ስ ሲጨመቅ ለስኳር መስሪያ የሚያገለግል ጣፋጭ ፈሳሽ የሚሰጥና በቆላማ አካባቢ የሚበቅል የአገዳ ተክል።

ሽንኩሬ ስ ሴቶች የሚጠሩበት የተዛምዶ ወይም የአክብሮት ስም።

ሽንኮር ስ በሽንኮራ አገዳ አምሳያ የተቀረፀ ወይም የታነፀ የአልጋ እግር።

ሽንኮፍ "ሰንኮፍ" ን ተመ.

ሽንዳራ ቅ (ስድብ) አይነ ሽውራራ፣ ጠንጋራ።

ሽንጋራ "*ሸነገረ" ስር ተመ.

ሽንጋይ "ሸነገለ" ስር ተመ.

ሽንጎ "ሸነጓ" ስር ተመ.

ሽንጎበት ስ የአገጭ ላይ ጢም።

ሽንጎበታም ቅ ጢማም።

ሽንጎኛ "ሸነጓ" ስር ተመ.

ሽንጥሮ ስ ሸለቆ።

ሸኘ ግ 1. አሰናበተ። 2. መንገደኛን በማጀብ ጥቂት መንገድ ወይም የተወሰነ ርቀት አብሮ ሄደ። 3. (ባለጉዳይን) አስተናግዶ ጉዳዩን ፈፅሞ እንዲሄድ አደረገ።

መሸኛ ስ 1. ዘመድ፣ ወዳጅ፣...ለመሸኘት የሚደረግ ግብዣ። 2. ሸኚ ደብዳቤ።

ሸኚ ቅ አጃቢ።

ሸኚ ደብዳቤ (መሸኛ ደብዳቤ) ስ አንድ ሰው፣ እቃ፣ ጉዳይ፣...ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ በሚላክበት ጊዜ ስለሁኔታው እንዲገልፅ በአጭሩ ተዘጋጅቶ ከተላኪው ጋር አብሮ የሚሄድ ደብዳቤ ወይም ፅሁፍ።

ተሸኘ ግ 1. ተሰናበተ፣ ሄደ። 2. መሸኛ ተደረገለት።

***ሸከመ**

ሸክም ስ 1. በሰው ጀርባ፣ ትከሻ፣ ራስ፣... ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ የሚጓጓዝ እቃ ወይም ጭነት።2.ክብደት፣ ጫና፣...ያለውና የሚያስቸግር ወይም የሚያስጨንቅ ማንኛውም ጉዳይ። 3. (ዘይ.) ራሱን ያልቻለ፣ የሌላ ሰው ጥገኛ ሆኖ የሚኖር (ሰው)።

ሸክም ነው ብዙ ነው። *በሃያ አምስት ብሮቲም የገዛችው ሽንኩርት ሸክም ነው።*

ተሸከመ ግ 1.ክብደት ያለውን ነገር በራሱ፣ በትከሻው፣ በጀርባው፣ ያዘ። 2. (ዘይ.) ተቀበለ፣ ቻለ፣ ታገሰ። *ይህን ሁሉ ችግር ተሸክሞ ኖሯል።*

ተሸካሚ ስ እቃ በጫንቃው ይዞ የሚያጓጉዝ ኩሊ።

አሸከመ ግ 1. እቃን በተሸካሚው ትከሻ ወይም ራስ፣... ላይ አደረገ። 2. በብዛት ሰጠ።

***ሸከረከረ**

ሽክርክር ስ ተሽከርካሪ ነገር።

ሽክርክሪት ስ 1. ከገል፣ ከቅል፣ ከቀንድ ወይም ከእንጨት ክብ ሆኖ የሚሰራ የእንዝርት ራስ። 2. በሞተር ወይም በነፋስ ሃይል የሚሽከረከር ውልብልቢት ወይም ክብ ሆኖ የተሰራና እንደ ጎማ የሚሽከረከር ነገር።

ተሽከረከረ ግ 1. ዞረ፣ ሾረ። 2.(ዘይ.) ወዲያ ወዲህ አለ፣ ተዘዋወረ፣ ሄደ። *አርፈህ ተቀመጥ አትሽከርከርብኝ።*

ተሽከርካሪ ስ መኪና ወይም እንደ መኪና በጎማ አማካይነት የሚንቀሳቀስ መጓጓዣ።

አሽከረከረ ግ 1. አሾረ፣ አዞረ። 2. (መኪናን፣ ብስክሌትን፣...) ነዳ። 3. (ዘይ.) በሚፈልገው አቅጣጫ አስኬደ።

አሽከርካሪ ስ መኪና ነጂ፣ ሹፌር።

ሸከሸከ ግ 1. ገለባን፣ ቂንድን ወይም እሰርን ከፍሬው ለመለየት እህልን በሙቀጫ ላላ አድርጎ ወቀጠ። 2. (ማግን፣ ሹራብን፣...) ጥብቅት እንዳይኖረው ዘርዛራ አድርጎ ሰራ። 3. በሳሳ፣ ወጋጋ።

ሽክሻካ ቅ 1. ዘርዛራ፣ ሳይጠብቅ ተራርቆ የተሰፋ፣ ስግስግ(ልብስ)። 2. (ዘይ.) ወሬኛ፣ ምስጢር የማይቋጥር፣ ቁምነገር የሌለው።

ሽክሽክ ቅ 1. ሳይደርቅ የተወቀጠ፣ ገለባውና ቂንዱ የተለየለት (እህል)። 2. ሳይጠብቅ ዘርዛራ ሆኖ የተሰፋ ወይም የተሰራ (ልብስ፣ ዳንቴል፣...)።

ተሽከሸከ ግ 1. በሙቀጫ ላላ ተደርጎ ተወቀጠ። 2. ሳይጠብቅ ዘርዛራ ሆኖ ተሰራ ወይም ተሰፋ (ልብስ)።

አሽከሸከ ግ ሸከሸከ፣ ላላ አድርጎ ወቀጠ።

ሽከኛ "ሽክ^1" ስር ተመ.

ሸከከ ግ ፈራ፣ ተጠራጠረ።

ሽክ ስ 1.ፍርሃት፣ ጥርጣሬ።2.ክፋት፣ ተንኮል።

ሸከፈ ግ የተበታተነውን ነገር ባንድ ላይ ሰበሰበ።

ሽክፍ ቅ 1.የተሰበሰበ።2. ጠንቃቃ።

ሸካራ "ሻከረ" ስር "ሻካራ" ን ተመ.

ሽክ^1 ስ ክፋት፣ ተንኮል።

ሽከኛ ቅ ክፉተኛ፣ ተንኮለኛ።

ሸክ^{2} "ሸከከ" ስር ተመ.

***ሸክ**

ሸክ አደረገ ግ ቀረጠ፣ ጎመደ (በስለት)።

ሸክላ ስ 1. እንደ ጀበና፣ ገበር ምጣድ፣ እንስራ፣...ያለ የቤት ቁሳቁስን ለመስራት የሚያገለግል የተለያዩ የአፈር አይነቶች ውሁድ። 2. ከሸክላ አፈር የሚሰራ እንደ ጀበና፣ ምጣድ ያለ እቃ። 3. ለቤት ህንፃና ለወለል ንጣፍ የሚያገለግል ጡብ። 4. ድምፅ የሚቀረፅበትና የተቀረፀውም ድምፅ በሸክላ ማጫወቻ አማካኝነት ተመልሶ የሚደመጥበት ክብና ዝርግ ነገር። 5. (ዘይ.) በቀላሉ የሚሰበር፣ ጥንካሬ የሌለው።

ሸክላ ማጫወቻ ስ በሸክላ ላይ የተቀረፀን ድምፅ ወይም ሙዚቃ ለማዳመጥ የሚያስችል በኤሌክትሪክ ሃይል የሚሰራ መሳሪያ።

ሸክላ ሰሪ ስ እንደ ጋን፣ ምጣድ ያሉትን የሚሰራ ሰው።

ሸክላ ሳህን ስ ከሸክላ የሚሰራ ዝርግ ወይም ጎድጓዳ ሳህን።

ሸክላ ስራ ስ የሸክላ ዕቃዎችን የማምረት ስራ።

[የ]ሸክላ እቃ እንደ የቡና ጀበና፣ የእንጀራ ምጣድ ያለ ከሸክላ የሚሰራ እቃ።



1. ጋን
2. እንስራ
3. ማሰሮ
4. ጣባ

5. ጊርጊራ
6. ጀበና
7. ሸክላ ድስት
8. ምጣድ

ሸክላ በቅሉ ስ ቀይ በቅሉ።

ሸክላ ቤት ስ ግድግዳው በጡብ የተሰራ ቤት።

ሸክም "*ሸከመ" ስር ተመ.

ሸክሻካ "ሸከሸከ" ስር ተመ.

***ሸኮመኮመ**

ሸኩምኩም ቅ ተሸኮርማሚ፥ አይን አፋር።

ተሸኮመኮመ ግ 1. ተሸኮረመመ። 2. ተማደረደረ።

አሸኮመኮመ ግ1. አሸኮረመመ፡ አቆላመጠ። 2. (ለአውራ ዶሮ) በአፉ ምግብ ይዞ ክንፉን በእግሩ አኳያ ዘርግቶ በእንስቷ ዶሮ ዙሪያ ተሽከረከረ።

***ሸኮረመመ**

ተሸኮረመመ ግ በአይን አፋርነት ጠባይ አይኑን ሰበር አንገቱን ዘንበል አደረገ፥ ተቅለሰለሰ።

አሸኮረመመ ግ 1.አቆላመጠ፡ አባባቀ፡ አቃበጠ፥ ተዳራ፤ በጥቅሻ፡ በቀልድ፥... አጫዋወተ። 2. አይኑን ሰበር አንገቱን ዘንበል አደረገ፡ አቅለሰለሰ።

***ሸኮተ**

ሽኩቻ ስ 1. ተወዳዳሪዎች በእጅ ጣታቸው አማካይነት የተለያየ ቅርፅ እየሰሩ (የወስፌ፣ የመቀስ፥...) ሁሉም በአንድ ጊዜ ብቅ አድርገው በማሳየት የሚያካሂዱት የቁማር ጨዋታ አይነት (ለምሳሌ. መቀስ ወስፌን፡ ሰይፍ መቀስን፡... ይረታል)። 2. (አንዱ ሌላውን ለመጣል፡ ለማሸነፍ የሚያደርገው) ፉክክር፥ ውድድር፡ ትግል፡ ሽሚያ።

ተሻኮተ ግ 1. ተወዳደረ፡ ተፎካከረ። 2. አጋና ተማታ።

አሻኮተ ግ 1. አወዳደረ፡ አፎካከረ። 2. አጋና አማታ።

ሸኮና "ሸሆና" ን ተመ.

ሸወረረ ግ ጠነገረ፡ ሸነደረ (አይን)።

ሸውራራ ቅ ጠንጋራ፥ አይኖቹ ወደሁለት የተለያዩ አቅጣጫዎች የሚመለከቱ የሚመስሉ።

ሸውረር አለ ግ ተጠናገረ፡ ተንሸዋረረ (አይኑ)።

ሸውረር አደረገ ግ አጠናገረ፡ አንሸዋረረ (አይኑን)።

ተንሸዋረረ ግ አይኖቹ ወደ ተለያየ አቅጣጫ የሚመለከቱ መሰለ።

አንሸዋረረ ግ አጠናገረ፡ አይኖቹን ወደተለያየ አቅጣጫ የሚመለከቱ አስመሰለ።

ሸወከ ግ ሰበቀ፥ አዋሸከ።

ሸውክ ስ ሰብቅ።

ሸውከኛ ቅ ሰብቀኛ፡ አዋሻኪ።

አዋሸከ ግ አሳበቀ፡ አጣላ።

ሸወደ ግ (የአራዳ አነ.) አታለለ፥ አሞኘ።

ሸዋጅ ቅ አታላይ።

ሸወዳ ስ ማታለል፡ ማሞኘት።

ተሸወደ ግ ተታለለ፥ ተሞኘ።

ሸውራራ "ሸወረረ" ስር ተመ.

ሸውሸዌ ስ ንፋስ ሲነካው ሸው ሸው የሚል የዛፍ አይነት።

ሸውሻዋ ቅ ከአንድ የማይረጋ፡ ወላዋይ፡ ከውካዋ።

ሸውከኛ "ሸወከ" ስር ተመ.

ሸውክ ዝ.ከ.

ሸዬ (ሾዬ) ስ ከታች ሰፋ፤ ከጫፉ ሾጠጥ የሚልና የሚበላ ፍሬ ያለው ትልቅ የዛፍ አይነት። "እሼግም ይባላል።

ሸደሸደ ግ 1. ሰፋ፥ ወሰወሰ፡ ሸከሸከ፥ ዘርዛራ አድርጎ ሰራ። 2. አፋጠነ፥ አጣደፈ። 3. አስቀመጠ፥ ነዳ (ተቅማጥ)።

ተሸደሸደ ግ ተሸከሸከ፥ ዘርዛራ ተደርጎ ተሰራ ወይም ተሰፋ።

***ሸገሸገ**

ሽግሽግ ስ ማጠጋጋት፥ማቻቻል፡ ማብቃቃት።

ተሸጋሸገ ግ ተጠጋጋ፥ ተቻቻለ፥ ተብቃቃ።

አሸጋሸገ ግ አጠጋጋ፡ አቻቻለ፡ አብቃቃ።

ሸገነ ግ አማረ፤ ተዋበ።

ሸገና ቅ መልከ መልካም፥ ሸጋ።

ሸጋ ቅ ያማረ፥ ቆንጆ፡ ውብ የሆነ።

አሸገነ ግ አሳመረ፡ አስዋበ።

ሸጉራ (ሻጉራ) ቅ አመሉ ከሰው የማይገጥም፡ አመለ ወልጋዳ።

ሸጎረ ግ 1. ቀረቀረ፥ ሸጎጠ፤ ደነቀረ። 2. ቆለፈ፡ ዘጋ።

መሸጎሪያ ስ (የበር፥ የሳጥን) መቀርቀሪያ።

ተሸጎረ ግ 1. ተቀረቀረ፥ ተሸጎጠ። 2. (በሩ) ተቆለፈ፡ ተዘጋ።

ሸጎበ ግ 1.(ውሻ) ጅራቱን ወደ ጉያው ከተተ፥ ወይም ሸጎጠ። 2. (ዘይ.) በትንሹ፥ ሰውር አድርጎ ሰጠ (ገንዘብን ለዘመድ፡ ጉቦ)።

ሸጎጠ ግ 1. ሻጠ፥ ወተፈ፡ አገባ። 2. ሰወረ፥ ደበቀ፡ ሸሸገ።

ሽጉጥ ስ 1.ከወገብ ላይ ወይም ከብብት ስር የሚታጠቁትና በአንድ እጅ የሚተኮስ አነስተኛ የጦር መሳሪያ።2. ግማሽ ሊትር የሚይዝ ትንሽ

ጠርሙስ፡ ቢራ ጠርሙስ።



ሽጉጥ

ሽጉጡን ጠጣ በሽጉጥ ራሱን ገደለ።

ሽጉጥ ታጠቀ ሽጉጥ አንገደረ፥ አነገበ (በወገብ፡ በብብት ስር)።

ሽጉጥ አለ ግ ተሸጎጠ፡ ተጠጋ (ተገን፡ ረዳት ፍለጋ)።

ተሸጎጠ ግ 1. ተሻጠ፥ ተወተፈ። 2. ተሰወረ፡ ተደበቀ፥ ተሸሸገ።

ሸጠ ግ 1. አንድን ነገር ወይም እቃ በገንዘብ ለወጠ። 2. (ዘይ.) ለጥቅም ሲል አሳልፎ ሰጠ። *የሃገሩን ምስጢር የሚሸጥ ከሃዲ ነው።* 3. (የአራ.ዳ አነ.) አታለለ፥ አሞኘ።

መሸጫ ስ 1. አንድ ነገር ወይም እቃ የሚሸጥበት ዋጋ። 2. እቃ ወይም ሌላ ነገር የሚሸጥበት መደብር።

ሻጭ ቅ አንድን ነገር ወይም እቃን በገንዘብ የሚሸጥ ወይም የሚለውጥ።

ሽያጭ ስ 1. አንድ ነገር ወይም እቃ የሚሸጥበት ዋጋ። 2. የአሻሻጥ ሁኔታ።

ተሸጠ ግ 1. በገንዘብ ተለወጠ። 2. (የአራ.ዳ.አነ.) ተታለለ፡ ተሞኘ።

አሸጠ ግ አንድን ሰው ንብረቱን፥ እቃውን እንዲሸጥ አደረገ ወይም ገፋፋ።

አሻሻጠ ግ ገገርን በማምጣት፡ በመደለል፡ በማግባባት እቃው ወይም ንብረቱ እንዲሸጥ አደረገ።

አሻሻጭ ስ 1. ደላላ። 2. ቡና ቤት የምትሰራ ሴት።

ሸጠሸጠ ግ በፍጥነትና በብዛት ሰራ፡ አደረገ፡ ፃፈ፥ አዘጋጀ፡...።

ሸጥ ስ ፈፋ፥ ፈረፈር።

ሸፈራ ስ በቆላ አካባቢ የሚበቅል የዛፍ አይነት።

ሸፈሸፈ ግ በመደዳ አጨደ፥ ቆረጠ፡ ከመከመ፡ አስተካከለ፡ ከረከመ።

ሽፍሻፊ ስ 1. ፍቅፋቂ፡ ቁርጥራጭ፡ ትርፍራፊ። 2. መናኛ ሳንቃ፥ ጠርብ።

ሸፈተ^{1} ግ አመፀ፡ ከዳ፥ ተሰየ፤ ወደ ዱር ወይም ወደ በረሃ ገባ ወይም ለመንግስት አልገዛ አለ።

ሽፍታ ስ አመፀኛ፥ ወንበዴ፥ ቀማኛ።

አሸፈተ ግ አሳመፀ፡ አስከዳ።

ሸፈተ^{2} ግ (በሚናጥ ወተት ላይ) ቅባቱ ከላይ ሰፎ እንደ ጤፍ ፍሬ ጉብጉብ ብሎ ታየ።

ሽፍታ ስ በሚናጥ ወተት ላይ ሰፎ የሚታይ ጤፍ የሚያክል ቅባት።

ሸፈነ ግ 1. አለበሰ፡ ከለለ፡ ጋረደ፡ እንዳይታይ አደረገ። 2. ደበቀ፡ ሰወረ። 3. ተክቶ ሰራ። *እሱ በሌለበት ጓደኞቹ ስራውን ሸፈኑለት።* 4. ቻለ፡ አጠቃለለ፥ ከፈለ። *ለትምህርት ቤት የሚያስፈልገውን ወጪ ሸፈነለት።*

መሸፈኛ ስ የመሶብ፡ የሳህን፡...ልብስ።

ሽፋን ስ 1. ልባስ፡ ክዳን፡ ከለላ። 2. ሰበብ፡ ምክንያት።

ሽፍን ቅ የተከደነ፡ ድብቅ።

ሽፍን ጫማ ስ እግርን ሙሉ ለሙሉ የሚያለብስ ጫማ።

ሽፍንፍን ስ 1. ድብቅ። 2. እንጀራ ለብሶ የሚቀርብ የስጋ ወጥ።

ሸፋፈነ ግ እንዳይታወቅ ወይም እንዳይጋለጥ ደበቀ።

ተሸፈነ ግ 1. ጨርቅን በመልበስ ተከለለ፡ ተጋረደ። 2. ተደበቀ፡ ተሰወረ፡ እንዳይታወቅ ሆነ። 3. (ስራው በሌላ ሰው) ተካሄደ፡ ተከናወነ። 4. (ወጪ) ተከፈለ፡ ተጠቃለለ።

ተሸፋፈነ ግ 1. ለበሰ፥ ተከናነበ። 2. (ገበናው፡ ምስጢሩ) ተለባበሰ፥ ተደበቀ፡ እንዳይታወቅ ተደረገ።

ሸፈጠ ግ 1. ከዳ፥ ካደ፥ አበለ፡ ዋሸ። 2. (ቁስሉ) የዳነ መስሎ እንደገና ተባባሰ።

ሸፋጭ ቅ አጭበርባሪ፡ አታላይ።

ሽፍጥ ስ 1. ክህደት፡ እብለት፡ ውሸት። 2. ማጭበርበር።

ሸፍጠኛ ቅ 1. ከዳተኛ። 2. አጭበርባሪ።

ሸፈፈ ግ ተወላገደ፥ ተጣመመ።

ሽፋፋ ቅ (ስድብ) እግረ ወልጋዳ፡ ጠማማ፡ በትክክል የማይረግጥ።

ሽፎ ገመዳ (ስድብ) እግሩን እያወላገደ ወይም እያጋመደ የሚሄድ።

ሸፈፍ አለ ግ ጠመም አለ፡ ወልገድ አለ።

ሸፈፍ ሸፈፍ አለ ግ ወልገድ ወልገድ እያለ ሄደ።

ተንሻፈፈ ግ ተወላገደ፡ ተጣመመ፤ በትክክል የማይረግጥ ሆነ።

አንሻፈፈ ግ አጣመመ፡ ሽፋፋ አደረገ።

ሽፋፊን "ሸፈነ" ስር ተመ.

ሽፋፋ "ሸፈፈ" ስር ተመ.

ሽፋጭ "ሸፈጠ" ስር ተመ.

ሽፍት ስ የበሬ የሽንት መሽኛው (የቀዳዳው) ዙሪያ::

ሽፍጠኛ "ሸፈጠ" ስር ተመ.

ሽፍጥ ዝ.ክ.

ሽፎ ገመዳ "ሸፈፈ" ስር ተመ.

ሹ የ'ሸ' ፊደል ካእብ ዘር::

ሹሉዳ "ሹልዳ" ን ተመ.

ሹል "ሾለ" ስር ተመ.

ሹልክልክ "ሾለከ" ስር ተመ.

ሹልውልዊት ስ ጅራቱ ጎፋሳ የሆነችና በዛፍ ላይ የምትኖር አይጥ የምትመስል አውሬ::

ሹልዳ(ሹሉዳ) ስ በታናሽ የሲጋ ብልት ላይ የሚገኝ ገርጣ ያለ ቀይ የስጋ ብልት::

ሹመት "ሾመ¹" ስር ተመ.

ሹም ዝ.ክ.

ሹም ሽር ዝ.ክ.

ሹሩባ "ሸረበ" ስር ተመ.

ሹራብ ስ ከጥጥ፣ ከሱፍ፣...ክር የሚሰራና ከወገብ በላይ ያለውን የሰውነት ክፍል የሚያለብስ፣ ባለ እጅጌና ባለኮሌታ ወይም ያለእጅጌና ኮሌታ የሚዘጋጅ የልብስ አይነት::

ሹርባ "ሸረበ" ስር "ሹሩባ"ን ተመ.

ሹርቤ ብርሌ "ሸረበ" ስር ተመ.

ሹሮ "ሽሮ"ን ተመ.

ሹሻይ ስ ቡና ወይም የቢሜና ቡና ድብልቅ መልክ ያለው፣ በመጠን ጨረባ የሚያክልና የሚመገባቸውን ነፍሳት እሾህ ላይ ከሰካ በኋላ የሚበላ ወፍ(ስእሉን ወፍ ስር ተመ.)::

ሹካ ስ ከብረት ወይም ከፕላስቲክ፣... የሚሰራ፣ ሶስት ወይም ከሶስት የበለጠ መውጊያ ጣት ያለውና ምግብን ለመጉረስ የሚያገለግል ባለ እጀታ እቃ::

ሹካ

ሹክ

ሹክታ ስ በቀስታ ወይም በጆሮ የተነገረ ምስጢር፣ ወሬ፣ ስብቅ::

ሹክሹክታ ስ 1. ሹክታ:: 2. በአነስተኛ ድምፅ የሚደረግ ንግግር:: 3. በአደባባይ ያልተነገረና ያልተረጋገጠ ወሬ::

ሹክ አለ ግ ሰው ሳይሰማ በቀስታ በጆሮ ወሬን ነገረ::

ተንሾካሾከ ግ ቀስ እያለ በምስጢር አወራ፣ ተነጋገረ::

አሾከሾከ ግ 1. ሌላ እንዳይሰማበት ቀስ ብሎ በለሆሳስ አወራ:: 2.አሳበቀ::

አሾክሿኪ ቅ አሳባቂ፣ ወሬኛ::

አንሾካሾከ ግ ቀስ ብሎ በምስጢር ነገረ፣ አወራ::

ሹግ (ሽግ) ስ ችቦ::

ሹጥ ስ (ፀያፍ) የኮሶ ትል::

ሹጣም ቅ (ፀያፍ፣ ስድብ) ሹጥ ያለበት (ሰው)::

ሹፌር "ሾፈረ" ስር "ሾፌር" ን ተመ.

ሺ የ"ሸ" ፊደል ሳልስ ዘር::

ሺህ (ሺ) ስ 1. ከዘጠኝ መቶ ዘጠና ዘጠኝ ቀጥሎ የሚመጣ ቁጥር፣ በአሃዝ ሲፃፍ ፲፻ :1000 ነው:: ቅ 2. መጠኑ አስር መቶዎችን የሆነ::*ሺህ ብር::*

ሻ¹ የ"ሸ" ፊደል ራብእ ዘር::

ሻ² ግ ፈለገ፣ አሰኘው:: *ለመሄድ ይሻል::*

ሲሻኝ ስፈልግ፣ ሲያሰኘኝ::

ቢሻው ቢፈልግ:: *ቢሻው ይምጣ:*

ኣሻ ግ አስፈለገ፣ አሰኘ:: *ምን ኣሻህ ? ምንም ኣልሻም::*

ምን ኣሻህ 1. ምን ቸገረህ፣ ምን አገባህ:: 2. ምን አሰኘህ፣ አስፈለገህ::

ኣያሻም አያስፈልግም:: *እንዲህ ያለ ነገር ኣያሻም::*

ያሻው ቢሆን የፈለገው ቢሆን፣ የመጣው ቢመጣ::

ሻሁራ "ሻኹራ" ን ተመ.

ሻህላ "ሻክላ" ን ተመ.

ሻህኝ ስ ብዙውን ጊዜ አፍንጫ ላይ የሚወጣ የቁስል አይነት::

***ሻለ**

ሻል አለ ግ ከበፊቱ የበለጠ ጥሩ ሆነ::

ሻል አለው (አገገመ፣ በመጠኑ ቡን ወይም ደህና ሆነ፣ ከህመሙ ዳነ::

ተሻለ ግ 1. በለጠ፣ ላቀ:: 2. ህመሙ ለቀቀ፣ በመጠኑ ተወገደ:: *መድሃኒት ወስጄ ህመሙ ተሻለኝ::*

የማይሻል የማይበልጥ፣ ከበፊቱ ለውጥ

የሌለው። *ለዚህ የመጣውም እቃ ከበፊቱ የማይሻል ነው።*

ተሻሻለ ግ 1. የተሻለ ሆነ፡ ጥሩ ለውጥ አሳየ። 2. በኑሮ፥ በስልጣኔ፡ በሃብት አደገ፥ በለፀገ። 3. ተለወጠ፤ መጠኑ፡ ጥራቱ፡ ደረጃው ከፍ ወይም ዝቅ አለ። *ዋጋው ተሻሽሏል።*

አሻለ ግ በጎ አደረገ፤ አዳነ፡ ህመሙን አስታገሰ።

አሻሻለ ግ 1. ለወጠ፥ ጥሩ አደረገ፡ አሳመረ። 2. መጠኑን፡ ጥራቱን፡ ደረጃውን ከፍ ወይም ዝቅ አደረገ።

ማሻሻያ ስ 1. ማስተካከያ፥ እርምት። 2. (የትምህርት፡ የደሞዝ፡ የዋጋ፡...) ደረጃን ከፍ ወይም ዝቅ ማድረጊያ።

ሻለቃ ስ 1.ከሻምበል በላይ ቀጥሎ ያለው ወታደራዊ ማእረግ። 2. የተወሰነ ብዛት ያለው ሰራዊት የሚገኝበት የወታደር ክፍል።

ሻል ስ ብዙውን ጊዜ ከለስላሳና ከሚሞቅ የጨርቅ አይነት ወይም ከሱፍ ክር የሚሰራና ሴቶች ትከሻቸው ላይ ጣል የሚያደርጉት አነስ ያለና እንደነጠላ የሚያገለግል ልብስ።

ሸሚት ስ ገፈራ፥ መኛ።

ሻማ¹ ስ 1. ከሰምና ከክር የሚሰራና ሲለኮስ ብርሃን የሚሰጥ ወፍራም የጧፍ አይነት። 2. የኤሌክትሪክ አምፖሎች የብርሃን መጠን ወይም አቅም መለኪያ። *ባለሃምሳ ሻማ አምፑል።*

ሻማ² ስ ናይሎንነት ያለው ጨርቅ።

*ሻማ

ሽሚያ ስ አንድን ነገር ለማግኘት፥ ለመውሰድ፥ለመንጠቅ መሽቀዳደም፡ መረባረብ።

ተሻማ ግ 1. አንድን ነገር ለመውሰድ፥ ለመያዝ ከሌላው ጋር ተወዳደረ፤ ተሽቀዳደመ፤ ተናጠቀ። 2. ተጋራ።

አሻማ ግ 1. አናጠቀ፤ የቀደመ፥ የቻለ፥ ያጋጠመው እንዲወስድ አወዳደረ። 2. ግልፅ አልሆን አለ፤ አቅጣጫውን የማይገልፅ፥ አጠራጣሪ ሆነ።

አሻሚ ቅ ግልፅ ያልሆነ፥ ከአንድ በላይ አማራጭ ያለው (ነገር)።

ሻሜ ስ የዶቃ አይነት።

ሻሜታ ስ ከበሶ የሚዘጋጅ ጌሾና ብቅል የሌለው ወፍራም መጠጥ።

ሻሜት ስ አጥሚት።

ሻምላ ስ ከነሃስ፥ ከብር ወይም ከሌላ ማእድን የሚሰራና ለክብር፥ ለጌጥ የሚያዝ ጎራዴ።

ሻምበል ስ 1. ከመቶ አለቃ ቀጥሎ የሚገኝ ወታደራዊ ማእረግ። 2. የተወሰነ ብዛት ያለው ሰራዊት የሚገኝበት የወታደር ክፍል።

ሻምፒዮን ስ የስፖርት ወይም የሌላ ውድድር የሁሉም አሸናፊ።

ሻምፓኝ ስ ብዙውን ጊዜ በሰርግ ወይም በሌላ ልዩ ዝግጅት ላይ ለእንግዳ ልዩ የክብር ወይም የደስታ መግለጫ ሆኖ የሚቀርብ ከወይን የሚዘጋጅና አልኮልነት ያለው መጠጥ።

ሻረ ግ 1. ዳነ፥ ተፈወሰ። 2. ተወ፡ አስቀረ፥ አፈረሰ። *የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔውን ሻረ።* 3. የመድሃኒት ሃይልን አጠፋ፡ ደመሰሰ፥ ቀነሰ። 4. ጣሰ፥ አፈረሰ። *ህጉን ሽሮ ወንጀል ሰራ።* 5. ከስልጣን አወረደ ወይም አስወገደ። 6. (ዘይ.) የሚበቃውን፥ የሚያረካውን ያህል አገኘ።

ሽረት ስ 1. ፈውስ፥ ድህንነት። 2. ከስልጣን መውረድ ወይም ማውረድ። 3. ከጠበቀት በላይ ማግኘት፡ መርካት (የውሳኔ፥ የፍርድ፥...)።

ተሻረ ግ 1. ከስልጣን ወረደ ወይም ተወገደ። 2. ተተወ፡ ቀረ፡ ፈረሰ። 3. ፈረሰ፡ ተገደፈ (ፆም)።

አሻረ ግ 1. አዳነ፥ ፈወሰ (የኮሶ መድሃኒት)። 2. ከተጠበቀው በላይ ሰጠ፡ አስደሰተ።

አሻረ ግ አስቀረ፡ አስለወጠ፡ አስገለበጠ (ውሳኔን፡ ፍርድን፡...)።

ሻሲ(ሻንሲ) ስ የመኪና የተለያዩ አነስተኛ ክፍሎች የሚገጣጠሙበትና ዋና ተሸካሚ የሆነ የራሱ መለያ ቁጥር ያለው ትልቅ የመኪና አካል።

የሻሲ ቁጥር ስ በሻሲ ላይ የታተመ መለያ ቁጥር።

ሻሽ ስ 1. ወርዱ ጠበብ ቁመቱ ረዘም ያለ፥ ከጥጥ የተሰራና ስስ የሆነ ነጭ የራስ ማሰሪያ፥ ጥምጥም። 2. ከጥጥ፥ ከሃር፥... የሚሰራ የተለያየ ቀለማትና መጠን ያለው የሴቶች የራስ ማሰሪያ ወይም ሽፋን።

ሻሽ የመሰለ በጣም ነጭ የሆነ።

ሻሾ ቅ የነጭ በሬ፡ ፈረስ፥... የቅፅል ስም።

ሻቀለ ግ 1. ጓጓ፥ ሰየ፥ ቋመጠ፥ ጎመጀ። 2.ቸኮለ፥ ተጣደፈ።

አሻቀለ ግ አጓጓ፥ አቋመጠ፥ አስጎመጀ።

*ሻቀበ

ሽቅብ ተግ. አቀበት፥ ወደላይ፥ ዳገት፥ የቁልቁል ተቃራኒ።

ሽቅብ ቁልቁል አለ 1. ወዲያ ወዲህ አለ፥ ተሯሯጠ፤ ለፋ፥ ደከመ፥ ኳተነ። 2. በተመሳሳይ ጊዜ ውስጥ አስመለሰ፥ አስቀመጠ።

ሽቅብ አለ አስታወከ።

ሽቅብ ወጣ ወደ ላይ አቅጣጫ ወይም ከፍ ወዳለ ቦታ ሄደ።

ሽቅበት ስ ዳገትማ፥ ከፍ ያለ ቦታ።

አሻቀበ ግ ወደላይ፥ ወደ ዳገት ወጣ ወይም ሄደ።

አሻቅቦ ተሳደበ ታላቁን ፥ የበላዩን ሰደበ።

*ሻተተ

ሽተቴ ስ ተቅማጥ።

ተንሻተተ ግ ተንሸራተተ፥ እየተንፏቀቀ ሄደ።

አንሻተተ ግ 1. አንሸራተተ፥ አዳለጠ። 2.(ተቅማጥ) አስቀመጠ።

ሻታ ስ 1.ተቅማጥ 2. (የአራዳ አነ.) ትውከት።

ሻንሲ "ሻሲ"ን ተመ.

ሻንቅላ ቅ ጥቁር።

ሻንቆ ቅ በጣም ጥቁር የሆነን በቅፅል ስም መልክ ለመጥራት የሚያገለግል ቃል።

ሻንቆ ጋሻ ስ ጌጥ የሌለውና ልሙጥ የሆነ ጥቁር ጋሻ።

ሻንኩራ ስ ባለ አንድ ጆሮ ማድጋ።

ሻንጣ ስ ከቆዳ፥ ከሸራ፥...የሚሰራ ቀላል ሳጥን።

ሻኛ ስ ከማጅራት ኋላ የሚገኝ ጉብ ያለ የበሬ ፥ የላም ... ትከሻ።

ሻከረ ግ 1. ኮሰኮሰ፥ ጎረበጠ፥ ቆረቆረ፥ ልስላሴ አጣ። 2. (ዘይ.) ደስ የማይል ሆነ፥ መጥፎ አዝማሚያ ያዘ። *በሁለቱ መሃል የነበረው ግንኙነት ሻክሯል።*

ሻካራ ቅ ለስላሳ ያልሆነ፥ የሚኮሰኩስ፥ የሚጎረብጥ።

አሻከረ ግ 1. ልስላሴ አሳጣ። 2.(ዘይ.) አስቀየመ፥ ቅር አሰኘ።

ሻኩራ (ሻሁራ) ስ 1. ከነሃስ፥ ከመዳብ፥... የሚሰራና የሚቅጨለጨል ወይም የሚንሿሿ መርገፍ ያለው የቤት ጉልላት ወይም በመሶብ ወርቅ ወይም በመረሻት ላይ ያለው የሚንሿሿ ዘርፍ። 2. የቤተክርስቲያን የማእጠንት እቃ፥ ፅንሃህ።

ሻካራ "ሻከረ" ስር ተመ.

ሻክላ (ሻህላ) ስ 1. ከብዙ አገልግሎት በኋላ የሚፈጠር የሸክላ እቃ የውስጠኛ ክፍል መቦርቦር ወይም መቀረፍ። 2.የደረቀ የጥርስ ልማም ወይም ቆሻሻ።

ሻክላ በላው ሻክላ አበላሸው፥ ቦረቦረው፥ ቀረፈው።

ሻወር ስ ውሃ በዝናብ መልክ እንዲወርድ የሚያደርግ ወንፊት መሰል ማውረጃ ከጫፉ ላይ የተገጠመበት የገላ መታጠቢያ ቧንቧ።

ሻይ ስ 1. ሞቃትና ርጥብ በሆነ አካባቢ የሚበቅል ቁጥቋጦ መሰል ተክል። 2. ሻይ ከሚባለው ተክል የሚገኘው ቅጠል ከውሃ ጋር ተፈልቶ፥ ብዙውን ጊዜ ስኳር ተጨምሮበት በትኩሱ የሚጠጣ፥ ቀላ ያለ መልክ ያለው መጠጥ።

የሻይ ማንኪያ ስ ሻይ ለማማሰል የሚያገለግል ትንሽ ማንኪያ(ስእሉን ማንኪያ ስር ተመ.)።

ሻይ ቅጠል ስ ደርቆና ደቆ የተዘጋጀ የሻይ ቅጠል።

ሻይ ቤት ስ ሻይ፥ ለስላሳ መጠጦችና ዳቦ፥... የሚሸጡበት የንግድ ቤት።

*ሻገረ

ሽግግር ስ ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ እስኪገባ ድረስ ያለው ጊዜ፥ ሁኔታ፥ ሂደት።

[የ]ሽግግር መንግስት ስ ቋሚ መንግስት እስኪመሰረት ድረስ በጊዜያዊነት የሚቋቋም መንግስት።

የሽግግር ወቅት ስ ከአንድ ደረጃ ወይም ሁኔታ ወደ ሌላ እስኪገባ ድረስ ያለው ጊዜ።

ተሻገረ ግ 1.(ወንዝን፥ ሸለቆን፥ ባህርን፥...) አቋርጦ ሄደ። 2. ተራመደ። 3. አለፈ። 4. ወደ ሌላ ገባ፥ ተላለፈ። 5. (በሽታ) ተጋባ፥ ተላለፈ።

ተሻጋሪ ግስ ስ ተሳቢ የሚያስፈልገው ግስ።

ተሸጋገረ ግ 1. አለፈ፥ ሄደ፥ አቋረጠ። 2. ከአንዱ ወደ ሌላ ተላለፈ። 3. እድገት፥ ለውጥ አሳየ። 4. (ከዘመን ወደ ዘመን) አለፈ፥ ተሻገረ። 5. (በውርስ) ተላለፈ።

መሸጋገሪያ ስ መተላለፊያ፥ መረማመጃ፥ ድልድይ፥ ርብራብ።

ተሸጋጋሪ ስ የቤትን ጣራ የሚሸከም ወፍራምና ረዥም እንጨት፥ ሰረገላ።

አሻገረ ግ 1.ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ አጓጓዘ ወይም ወሰደ። 2. (ድልድይ፥ መንገድ) መረጋገጫ ሆኖ አሳለፈ፥ አስኬደ። 3. ከአንዱ ወደ ሌላው አስተላለፈ። 4. ከአንዱ መነሻ ቦታ ወደ ሌላው ለመሄድ መተላለፊያው ወይም መንገዱ ችግር የሌለበት ሆነ።

ባሻገር 1. ወዲያ፥ በኋላ፥ ሌላ፥ በተጨማሪ። *ከዚህም ባሻገር ሌላ አገልግሎት ይሰጣል።* 2. በርቀት ወይም ማዶ። *ባሻገር የሚታየው የሰውየው ቤት ነው።*

ባሻጋሪ በርቀት።

አሻግሮ ተመለከተ በርቀት ያለውን ተመለከተ።

አሻጋሪ ስ ወንዝን የሚያሻግር ዋናተኛ።

አሸጋገረ ግ 1. አስተላለፈ። 2. አደረሰ። *እንኳን ከዘመን ወደ ዘመን አሸጋገረዎ*። 3. (ገመድን፥ ወራጅ እንጨትን) ከወዲህ ወደዚያኛው ዳር አስተላለፈ (ለማሰር፥ ለመምታት፥...)።

ሻገተ ግ 1. ሸበተ፥ ከመቆየት፥ ከሙቀት የተነሳ ተበላሸ (እንጀራ፥ ዳቦ፥...)። 2. ብዙ ኖረ ቆየ፥

ወይም አረጀ።

ሻጋታ ቅ 1. የታመቀ፣ ጥጥ የመሰለ፣ የተበላሸ (እንጀራ፣ ዳቦ፣...)። 2. (ስድብ) አሮጌ፣ የተበላሸ፣ ንፅህና የጎደለው።

ሻጉራ "ሽጉራ" ን ተመ.

ሻግያ ቅ በጣም ጥቁር የሆነ፣ ጠቋራ።

ሻጠ ግ ሰካ፣ ተከለ፣ ሸጎጠ፣ ሳተ።

ተሻጠ ግ ተሰካ፣ ተሸጎጠ።

ሻጠረ ግ 1. አዋዋለ፣ አስማማ፣ አገበያየ። 2. ተብለጠለጠ፣ ተንኮል፣ ሸር ሰራ።

ሻጥር ስ ተንኮል፣ ሸር።

ሻጥረኛ ቅ ተንኮለኛ፣ ሸረኛ።

አሻጠረ ግ ተንኮል፣ ሸር ሰራ፣ ደባ ፈፀመ።

አሻጥር ስ ተንኮል፣ ሸር፣ ሴራ፣ ደባ።

አሻጥረኛ ቅ ተንኮለኛ፣ ሸረኛ፣ ደባ የሚፈፅም።

ሻጭ "ሻጠ" ስር ተመ.

ሻፈደ ግ (ንውር) ቋመጠ፣ ፈለገ፣ ጓጓ (ለወሲብ)።

ሻፋዳ ቅ (ስድብ) ቅንዝረኛ፣ ሴሰኛ።

አሻፈደ ግ (ንውር) ለወሲባዊ ግንኙነት አግባባ፣ ቀሰቀሰ፣ አነሳሳ።

ሻፎ ቅ ስለት ያለው ሹል (ድንጋይ፣ ሱፋጭ፣ ባልጩት)።

ሼ የ"ሸ" ፊደል ሃምስ ዘር።

ሼህ "ሸህ" ን ተመ.

ሽ የ"ሸ" ፊደል ሳድስ ዘር።

-ሽ ከግሳዊ ቃል በስተመጨረሻ በኩል እየገባ፣ የግሱ ባለቤት ወይም ተሳቢ መደቡ 2ኛ፣ ቁጥሩ ነጠላ ፆታው አንስታይ መሆኑን የሚያመለክት ምእላድ። ለምሳሌ "መፅሃፉን ወሰድሽ?" በሚለው ግሳዊ ቃል ውስጥ "-ሽ" "አንቺ" የሚለውን የግሱን ባለቤት ያመለክታል። "ጠሩሽ" በሚለው ግሳዊ ቃል ውስጥ "-ሽ" "አንቺን" የሚለውን ተሳቢ የሚያመለክት ምእላድ ነው። ከላይ ከተጠቀሱት መረጃዎች (መደብ፣ ቁጥር፣ ፆታ) በተጨማሪ የአንድ ነገር ባለቤት ወይም ባለ ይዞታ መሆንን የሚያሳይ ምእላድ ነው። ለምሳሌ "መኪናሽ" በሚለው ቃል ውስጥ "-ሽ" "ያንቺ" የሚለውን የባለቤትነት ይዞታ ያሳያል።

ሽህር ስ መሲና፣ የደለበች የስጋ ላም።

ሽሉዳ "ሹልዳ" ን ተመ.

ሽላን ስ እንስላል።

ሽል ስ 1. ፅንስ። 2. (ዘይ.፣ ስድብ) ልፍስፍስ፣ ደካማ፣ አቅመቢስ(ሰው)።

ሽለሙቅ ቅ ቶሎ ቶሎ የምትፀንስና የምትወልድ (ሴት)።

***ሽል**

ሽል አለ ግ 1. ሰለለ፣ ቀጠነ። 2. (ተራ አነ.) ተደብቆ፣ ተሸሽጎ ሄደ።

ሽልማት "ሸለመ" ስር ተመ.

ሽልም ዝ.ከ.

ሽልምልም ዝ.ከ.

ሽልብታ "*ሸለበ" ስር ተመ.

ሽልጦ ስ እንደጢቢኛ ያለ ወፈር ያለ ቂጣ።

ሽልፋ ቅ 1. የማይረባ፣ አቅመቢስ። 2. በአይነቱ በጣም ዝቅተኛና ተራ የሆነ፣ መናኛ።

ሽመለኛ "ሽመል" ስር ተመ.

ሽመላ ስ እግረ ቀጭንና ረዥም የሆነ በየወንዙ ዳር የሚታይ የአሞራ አይነት (ለእሱን አሞራ ስር ተመ.)።

ሽመል ስ 1. እንደመቃ አንጓ ያለው ውስጠ ድፍን የሆነ የእፅዋት አይነት። 2. በትር፣ ዱላ።

ሽመለኛ ቅ ዱለኛ፣ ተደባዳቢ።

ሽሙንሙን "ሽሞነሞነ" ስር ተመ.

ሽሙጥ "*ሽሞጠጠ" ስር ተመ.

ሽሙጥጫ ዝ.ከ.

ሽሚያ "*ሻማ" ስር ተመ.

ሽማት(ሽማያት) ስ የቅማያት አባት ወይም እናት፣ አራተኛ አያት።

ሽማግሌ "ሸመገለ" ስር ተመ.

ሽምብሩት "ሽንብራ" ስር **"ሽንብሩት"**ን ተመ.

ሽምብራ "ሽንብራ" ን ተመ.

ሽምድምድ "*ሽመደመደ" ስር ተመ.

ሽምግልና "ሸመገለ" ስር ተመ.

ሽምጥ^{1} **"ሸመጠጠ**^{1}**"** ስር ተመ.

ሽምጥ^{2} **"ሸመጠጠ**^{2}**"** ስር ተመ.

ሽረት^{1} **"ሻረ**^{1}**"** ስር ተመ.

ሽረት^{2} **"ሻረ**^{2}**"** ስር ተመ.

ሽር

ሽር አለ ግ 1. ፈጠነ፣ ቀለጠፈ (ለስራ)። 2. ዘነጠ፣ ተሽቀረቀረ።

ሽር ጉድ አለ (ስራ ለመስራት፣ ለማስተናገድ) ወዲያ ወዲህ አለ።

ሽር ጉድ አበዛ አጉል ታዛዥነት፣ አለሁ አለሁ ባይነት አሳየ።

ሽርሙጥና "ሸረሞጠ" ስር ተመ.

ሽርሽር "ሸረሸረ^{2}**"** ስር ተመ.

ሽርቁጥ "ሽረቆጠ" ስር "ሽርቋጣ"ን ተመ.

ሽርቦሽ "ሽረበ" ስር ተመ.

ሽርካ "*ሽረከ" ስር "ሽሪክ" ን ተመ.

ሽርክ ዝ.ክ.

ሽርክርክ "*ሽረከረከ" ስር ተመ.

ሽርክት "ሽረከተ" ስር ተመ.

ሽርክና "*ሽረከ" ስር ተመ.

ሽርደዳ "ሽረደደ" ስር ተመ.

ሽርጥ "ሽረጠ" ስር ተመ.

ሽርፍ "ሽረፈ" ስር ተመ.

ሽርፍራፊ ዝ.ክ.

ሽሮ **(ሹሮ)** ስ ከተቆላ አተር፣ ባቄላ፣ ሽንብራ፣...ተፈጭቶ የሚዘጋጅ ለወጥ የሚሆን ዱቄት። 2. ከሽሮ ዱቄት የሚሰራ ወጥ።

ሽሽት "ሸሸ" ስር ተመ.

ሽሽግ "ሸሸገ" ስር ተመ.

ሽቀላ "ሸቀለ" ስር ተመ.

ሽቁምቁም "*ሸቆመቆመ" ስር ተመ.

ሽቁጥቁጥ "*ሸቆጠቆጠ^{1}" ስር ተመ.

ሽቅበት "*ሻቀበ" ስር ተመ.

ሽቅብ ዝ.ክ.

ሽበታም "ሸበተ" ስር ተመ.

ሽባ ስ 1.እግሩ ወይም እጁ እንደልብ ሊታዘዝለት የማይችል፣ ሰላላ፣ ልምሾ፣ አካለ ስንኩል።2. (ዘይ.) ልፍስፍስ፣ አቅም ወይም ጥንካሬ የሌለው (ሰው)።

ሽባጥ ስ በጣልቃ ወይም በጎደለ ቦታ የሚገባ ስርዋፅ።

ሽብልል **(ሽብል)** "ሸበለለ" ስር ተመ.

ሽብልቅ "ሸበለቀ" ስር ተመ.

ሽብልብል "*ሸበለበለ" ስር ተመ.

ሽብር "*ሸበረ" ስር ተመ.

ሽብርተኛ ዝ.ክ.

ሽብሽባ "*ሸበሸበ" ስር ተመ.

ሽብሽባት "ሸበሸበ" ስር ተመ.

ሽብሽቦ ዝ.ክ.

ሽቦ ስ እንደ ክር፣ ሲባጎ፣...ቀጭን ሆኖ የተሰራ ብረት፣ መዳብ...።

ሽቦ ራስ (ስድብ) ቁርንድድ ፀጉር።

ሽቦ አልጋ ስ ከብረትና ሽቦ የተሰራ አልጋ።

ሽቱ "ሸተተ" ስር "ሽቶ" ን ተመ.

ሽታ "ሸተተ" ስር ተመ.

ሽቶ ዝ.ክ.

ሽንሽና ስ በወንዝ ዳር የሚበቅልና የማይነቅዝ የዛፍ አይነት።

ሽንሽን "ሸነሸነ" ስር ተመ.

ሽንቁር "ሸነቆረ" ስር ተመ.

ሽንቅር ዝ.ክ.

ሽንቅጥ "ሸነቀጠ" ስር "ሽንቃጣ" ን ተመ.

ሽንብራ(ሽምብራ) ስ በጫፉ ላይ ሾል ያለ አፍንጫ መሰል ጉጥ ያለው ፍሬ የሚያፈራ የአበባ እህል፤ ፍሬውም "ሽንብራ"ይባላል።

ሽንብራው ፈሰሰ ህፃን በወደቀ ጊዜ እንዳያለቅስ ሃሳቡን ወደ ሌላ ለመውሰድ የሚባል የማባበያ ቃል።

ሽንብሩት **(ሽምብሩት)** ስ ሽንብራ የምትመስል የንብ አይነት።

ሽንብራ ዱቤ ስ ፍሬው ትልልቅ የሆነ ሽንብራ።

ሽንታም "ሸና" ስር ተመ.

ሽንት ዝ.ክ.

ሽንትራት "ሸነተረ" ስር ተመ.

ሽንትር ዝ.ክ.

ሽንኩርት ስ ቀላ ወይም ነጣ ያለ መልክ ያለው ክብ ሆኖ በመሬት ውስጥ የሚያፈራና የሚፋፋ የተነባበረ ቆዳ ያለው ተክል።

ቀይ ሽንኩርት

ነጭ ሽንኩርት

ሽንክ ስ ነጭ አባ ጨጓሬ የሚመስል ነፍሳት።

ሽንክላ ስ የውሃ፣ የጠላ፣...መያዣ ማድጋ።

ሽንገላ "ሸነገለ" ስር ተመ.

ሽንጥ ስ 1. በጀርባ አጥንት ግራና ቀኝ በኩል ከትከሻ ግርጌ እስከ ዳሌ አካባቢ ያለው የሰውነት ክፍል(ስእሉን ሰውነት ስር ተመ.)። 2. ከሻኛ ግርጌ እስከ ጅራት አካባቢ የሚደርስ የቀንድ ከብት የስጋ ብልት።

ሽንጣም ቅ ቁመቱ ረዥም የሆነ።

ሽንጥ ራስ ስ የሽንጥ ጫፍ ስጋ።

ሽንፈት "*ሸነፈ" ስር ተመ.

ሽንፍላ ስ 1. ፈርስ የሚቀመጥበት፣ ሲያጥቡት ቶሎ የማይጠራ የተነባበረና ትንንሽ ከረጢት

ያለው ወንራ መሰል የሆድ እቃ። 2. (ዘይ.) የማይጠራ፥ እንከን የማይታጣበት።

ሽኩምኩም “*ሽኮመኮመ” ስር ተመ.

ሽኩቻ “ሽኮተ” ስር ተመ.

ሽክ

ሽክ አለ ግ ተዋበ፣ አጌጠ።

ሽክርክሪት “*ሽከረከረ” ስር ተመ.

ሽክርክር ዝ.ክ.

ሽክሽክ “ሽከሸከ” ስር ተመ.

ሽክና ስ ከቅል የሚዘጋጅ የውሃ፣ የጠላ፥... መቅጃ ወይም መጠጫ እቃ።

ሽክፍ “ሽከፈ” ስር ተመ.

ሽኮኮ ስ በየጎሬው፥ በየቋጥኙ የሚኖር፥ ድመት የሚያክልና ቅርፁም ሆነ መልኩ አይጥ የሚመስል እግረ አጭር የዱር አውሬ(ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።

ሽወዳ “ሸወደ” ስር ተመ.

ሽው

ሽውታ ስ 1. የምች፥ የግርፋት ህመም። 2. የነፋስ እንቅስቃሴ (ፍጥነት)። 3. (ዘይ.) ጭምጭምታ ወሬ።

ሽው አለ ግ ኸው፣ ጭልጥ ብሎ ሄደ። 2. በፍጥነት በሮ አለፈ። 3. ነፈሰ፣ የነፋስ እንቅስቃሴ ተሰማ።

ሽው አለበት 1. በትንሹ ተጨመረበት። 2. ዞር አለበት፣ እንደመበሳሸት አለ (ጠላ፣ ጠጅ፥...)።

ሽው አለው 1. ጨረፍታ ወሬ ሰማ። 2.በመጠኑ አመመው።

ሽው ሽው አለ ግ 1.መላልሶ ነፈሰ። 2. ከነፈ፥ ወዲያና ወዲህ አለ፣ ተንከወከወ። 3. በነፋስ ሃይል ተንቀሳቀሰ፥ ተወዛወዘ (ዛፍ፥ ቅጠል)።

ሽያጭ “ሸጠ” ስር ተመ.

ሽጉጥ “ሸጎጠ” ስር ተመ.

ሽግል ስ የአባለ ዘር በሽታ፣ ጨብጥ።

ሽግሽግ “*ሸገሸገ” ስር ተመ.

ሽግግር “*ሸገረ” ስር ተመ.

ሽፉል ስ ከግንባር በታች ያለው የቅንድብ ፀጉር (በጎጃምና በጎንደር ቅንድብ እየተባለ ይጠራል) (ስእሉን አይን ስር ተመ.)።

ሽፋሽፍት ስ በአይን ዙሪያ ያለ ፀጉር። ቅንድብ እየተባለም ይጠራል(ስእሉን አይን ስር ተመ.)።

ሽፋን “ሸፈነ” ስር ተመ.

ሽፋፍ ስ ያስለት (የጦር፥ የቢላዋ፣ የቀስት፥...) ማህደር።

ሽፍ

ሽፍታ ስ ሽፍ ወይም እጅብ ብሎ የሚወጣ እከክ መሰል ነገር።

ሽፍ አለ ግ እጅብ ብሎ ወጣ፥ ታየ፥ በቀለ፥ አለበሰ (እንደ ቡቃያ ወይም እከክ ያለ ነገር)።

ሽፍሻፊ “ሸፈሸፈ” ስር ተመ.

ሽፍታ^{1} ስ ቀጭን ሹሩባ።

ሽፍታ^{2} “ሸፈተ^{1}” ስር ተመ.

ሽፍታ^{3} “ሸፈተ^{2}” ስር ተመ.

ሽፍታ “ሽፍ” ስር ተመ.

ሽፍት ስ ፈረቃ።

ሽፍን “ሸፈነ” ስር ተመ.

ሾ የ “ሸ” ፊደል ሳብእ ዘር።

ሾለ ግ ከወደ ጫፉ ቀጠነ፥ እንደ ወስፌ ሆነ፥ ሾጠጠ።

ሹል ቅ ከጫፉ የቀጠነ፣ የሾጠጠ።

ሹል አፍ ቅ (ስድብ) ነገረኛ፥ ምጥሚጣ።

አሾለ ግ ከጫፉ አቀጠነ፣ አሾጠጠ።

ሾለቅ ስ ምንቃሩ ትልቅ የሆነ የአሞራ አይነት (ስእሉን አሞራ ስር ተመ.)።

ሾለከ ግ 1.በቀዳዳ ወጣ፥ ተፈተለከ፥ ወሰቀ፥ አልፎ ሄደ። 2. ሳይታይ ቀስ ብሎ ሄደ፣ ጠፋ፣ አመለጠ። 3.ተረፈ፥ ዳነ፥ አመለጠ፥... (ከሞት፣ ከአደጋ፥...)።

መሹለኪያ ስ መውጫ፥ ማለፊያ፣ ቀዳዳ።

በሹልክታ ተው.ግ. ሳይሰማ፥ ሳይታይ፥ ሳይታወቅ።

ሾላኪ ቅ 1. (ስድብ) ቀትረ ቀላል፥ ከውካዋ። 2. ሰላይ።

ሹልክልክ ቅ (ስድብ) የማይያዝ፥ የማይጨበጥ፥ እርጋታ የሌለው።

ሹልክ አለ ግ ድምፁን ሳያሰማ፣ ሳይታይ ፈጥኖ ወጣ ወይም ሄደ።

ሹልክ አደረገ ግ አሾለከ።

ተሾለከ ግ ቀስ ብሎ ወይም ተደብቆ ወጣ ወይም ሄደ።

ተሽሎከሎከ ግ ውስጥ ለውስጥ ተጓዘ፥ አለፈ።

መሽሎክሎኪያ ስ ውስጥ ውስጡን መተላለፊያ መንገድ።

መሿለኪያ ስ ለመተላለፊያ የሚያገለግል ቀዳዳ ወይም ክፍተት።

አሽሎከሎከ ግ ውስጥ ለውስጥ አስኬደ፥ አሳለፈ።

አሾለከ ግ አስወጣ፥ አሳለፈ።

አሾለከ ግ እንዲሾልክ አደረገ።

ሾላ ስ ፍሬው የሚበላ ትልቅ ዛፍ፤ ፍሬውም ሾላ ይባላል።

ሾላ በድፍን ነገሩ ወይም ምስጢሩ ሳይገለጥ እንዳለ ይሁን ለማለት የሚነገር ኣባባል።

ሾሌ ስ አፉና ከንፈሩ ኣካባቢ ነጭ የሆነ ፈረስ፤ ኣፌ ሾሌም ይባላል።

ሾመ^1 ግ ስልጣን ሰጠ።

ሹም ስ ባለስልጣን፤ ኣለቃ፤ ኣዛዥ፤ ሃላፊ።

ሹም ሽር ስ በስልጣን የነበረውን የማውረድና ሌላ አዲስ ባለስልጣን የመተካት ተግባር።

ሹመት ስ የበላይ ሃላፊነት፤ የአዛዥነት፤ የአለቅነት፤ የአስተዳዳሪነት ማእረግ ወይም ስልጣን።

ሹመት አይደንግጥ ከስልጣን ለተሻረ ሰው የሚቀርብ የማፅናኛ አነጋገር።

ሹመት ኣገኘ ስልጣን አገኘ፤ ሃላፊነት ተሰጠው።

ሹመት ያዳብር (ምር.) ሹመቱ ይፅና፤ እያደገ ወይም ከፍ እያለ ይሂድ፤ ይጨምር (አዲስ ለተሾመ የሚቀርብ የደስታ መግለጫ)።

የሹመት ደብዳቤ ስ አንድ ሰው ለአንድ የስራ ሃላፊነት የተመደበ መሆኑን የሚገልፅ ደብዳቤ።

ሿሚ ቅ ስልጣን መስጠት የሚችል ከፍተኛ ባለስልጣን።

ተሾመ ግ ስልጣን፤ ሹመት ኣገኘ ወይም ተሰጠው።

ተሿሚ ቅ ከፍተኛ ማእረግ ወይም ስልጣን ያገኘ (ሰው)።

ኣስሾመ ግ ስልጣን ኣሰገኘ። *የሚያሾም ስራ ሰርቷል።*

ሾመ^2 ግ ሞላ፤ አንቸረፈፈ፤ ጢም አደረገ። *ጠላውን በጋን ሾመ።*

ተሾመ ግ ተሞላ፤ ተንቸረፈፈ፤ ጢም አለ (ጠጁ ወይም ጠላው በማድጋ፤ በጋን፤...)። 2. በሽታ፤ ዛር፤...በላዩ አደረ። *የተሾመበት ዛር ሓፋናኛር ሓለው።*

ሾረ ግ 1. ተሽከረከረ፤ ዞረ፤ ተንሻረረ። 2. (ዘይ.) ሀ. ታረመ፤ ተስተካከለ፤ ልክ ገባ። ለ. ሰለጠነ፤ ቀለጠፈ።

አሾረ ግ 1. ኣሽከረከረ፤ ኣዞረ፤ ኣንሻረረ። 2.(ዘይ.) ሀ. ኣረመ፤ አስተካከለ፤ ልክ ኣገባ። ለ. ቀልጣፋ አደረገ።

ሾርባ ስ በፈሳሽ መልክ የሚዘጋጅ የምግብ ኣይነት።

የሾርባ ማንኪያ ስ ከሻይ ማንኪያ ከፍ የሚልና ሁለት የሻይ ማንኪያ ያህል የሚይዝ ማንኪያ (ስእሉን ማንኪያ ስር ተመ.)።

የሾርባ ሳህን ስ ለሾርባ ማቅረቢያ የሚያገለግል ጎድጓዳ ሳህን።

ሾርኔ ስ የጎን፤ የእጅ ኣዙር፤ የተዘዋዋሪ መንገድ። *በሾርኔ ሰደበው።*

ሾቀ ግ 1.በመጠኑ ተቀቀለ፤ ተንገረገበ። 2. ራሰ፤ ረጠበ። *ልብሱ በዝናብ ሾቀ።* 3. በሙሉ ኣለቀ ወይም ሞተ። *ሰራዊቱ እንዳለ ሾቀ።*

ተሾቀ ግ ተንገረገበ፤ እንዲርስ፤ ተደረገ (በመጠኑ በመቀቀል)።

አሾቀ ግ 1. በመጠኑ ቀቀለ፤ አንገረገበ። 2. ኣራሰ፤ ኣረጠበ (ለምሳሌ ዝናብ ልብስን)።

ኣሹቅ ስ ተቆልቶ በፈላ ውሃ የተንገረገበ ባቄላ ወይም ኣተር።

ሾተላይ ስ የወንድና የሴት የደም ኣይነት ቅንጅት ተስማሚ ባለመሆኑ ሽሉ እንደተፀነሰ ወይም ህፃኑ እንደተወለደ እንዲሞት ያደርጋል ተብሎ የሚታመንበት የወሊድ ችግር።

ሾተሌ ስ እንደ ጭልፊት ያለ የኣሞራ ኣይነት።

ሾተል ስ በሁለት ወገን ስለት ያለው ቶፕ ያለ ቀጭን ሰይፍ።



ሾተል

ሾተል አፍ ቅ (ስድብ) ተሳዳቢ፤ ምላሰኛ።

***ሾከከ**

ሾካካ ቅ 1. (ስድብ) ኣሳባቂ፤ ወሬኛ። 2. ጥላ ቢስ፤ ቀላል።

ተንሿከከ ግ 1. ጥላ ቢስ ሆነ። 2. ኣሳበቀ፤ ወሬ ኣቀበለ።

ኣንሿከከ ግ አሳበቀ፤ ነገር ኣቀበለ።

ሾኬ ስ ሰውን በእግር ጠልፎ የመጣል ዘዴ።

ሾዬ "ሽዬ" ን ተመ.

ሾጠጠ ግ ከወደ ጫፉ ቀጠነ፤ ሞለለ፤ ሾለ።

ሾጣጣ ቅ ቀጭን ወይም ጠባብ፤ ሞላላ፤ ሹል የሆነ።

ኣሾጠጠ ግ ሞላላ፤ ሾጣጣ አደረገ።

ሾጤ ቅ ወገበ ቀጭን።

ሾጤ በርበሬ ስ ቀጭንና ረጅም የሆነ ቃሪያ፤ በርበሬ።

ሾጥ

ሾጥ ኣደረገ ግ በልምጭ፤ በኣለንጋ፤...

ሸንቆጠ፡ ገረፈ፡ መታ።

***ሾፈ**

ተሾፈ ግ ተቀለደ፡ ተዘበተ፡ ተፌዘ።

አሾፈ ግ 1. አፌዘ፡ ቀለደ። 2. ናቀ፡ አቃለለ።3. ለገመ፡ ዳተኛ ሆነ (በስራ)።

አሿፊ ቅ 1. ቀላጅ፡ ፌዘኛ። 2. በስራ ላይ የሚቀልድ፡ ለግመኛ።

ሾፈረ ግ መኪና ነዳ ወይም አሽከረከረ።

ሾፌር(ሹፌር) ስ መኪና ነጂ ወይም አሽከርካሪ።

ሿ የ "ሸ" ፊደል ፍንፅቅ ዘር።

ሿሚ "ሾመ" ስር ተመ.

***ሿሿ**

ሿሿቴ ስ 1. የገደል ላይ የውሃ ፏፏቴ ድምፅ። 2.የዕንሃህ፡ የፀናፅል፡ የሻኩራ፡ የመረሸት፡ የጉልላት፡... እቃዎች ወይም መርገፍ፡ ቅሲቃሴ የሚፈጠረው ድምፅ።

ሿ አለ ግ ተንሿሿ፡ የመፍሳት፡ የመፍሰስ ድምፅ ሰጠ።

ሿ አደረገ ግ በተን፡ አስገባ። *ጋዝ ያለበት ውሃ መጠጣት ሆድን ሿ ያደርጋል።*

ተንሿሿ ግ 1. ፈሰሰ፡ ገነፈለ። 2. የመፍሰስ፡ የመፍሳት ድምፅ አሰማ። 3. ተቅጨለጨለ።

አንሿሿ ግ 1. አቅጨለጨለ። 2. የመፍሰስ፡ የመፍሳት ድምፅ አሰማ።

ቀ

ቀ ከ "ሸ" ፊደል ዘር ቀጥሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል (ግእዝ ሆሄ)።

ቀለሀ (ቀለኻ) ስ ጥይቱ ከተተኮሰ በኋላ ወይም በሌላ ምክንያት ያለባሩድና ያለ አረሳስ የሚቀረው ባዶው ቀፎ(ስእሉን ጥይት ስር ተመ.)።

ቀለሀ ራስ ቅ (ስድብ) ባዶ፥ የማያስብ፥ የማያመዛዝን (ሰው)።

ቀለለ ግ 1. አነሰ፥ ቀነሰ፥ ክብደት አጣ። 2. ተዋረደ፥ አፈረ። *ውሸት ተናግሮ በህዝብ ፊት ቀለለ።* 3. የማያስቸግር ሆነ፤ ገራ። *ፈተናው ቀለለ።* 4. ተሻለ። *ህመሙ ከትናንት ዛሬ ቀለለው።* 5. ኮሰሰ፥ ዝቅ ብሎ ታየ።

ቀላል ቅ 1. ከባድ ያልሆነ። 2.(ስድብ) ወራዳ፥ ክብሩን የማይጠብቅ፥ ባለጌ።

በቀላሉ ተው.ግ. ያለብዙ ችግር፥ ድካም። *ችግሬን በቀላሉ ተወጣሁት።*

ቅለት ስ የመቅለል፡ ከባድ ያለመሆን ሁኔታ።

ቅሌት ስ ውርደት፥ የሚያሳፍር፥ ነውር ስራ።

ቅሌታም ቅ (ስድብ) ወራዳ፡ ነውረኛ።

ተቃለለ ግ 1. ቀስ በቀስ ክባዱ እየተነሳለት አነሰ፥ ቀነሰ። 2. ተጣፋ፡ ተካፈለ። *2/4ኛ ሲቃለል ½ ይሆናል።* 3. መፍትሄ አገኘ፥ ችግሩ ተወገደ።

አቃለለ ግ 1. አዋገደ፥ አገባደደ (ስራን)። 2. (ሂሳብን)አጣፋ፥ አካፈለ። 3. መፍትሄ ሰጠ፥ አስወገደ (ችግርን)። 4. ናቀ፥ አኮሰሰ፥ አዋረደ።

ቀለመ^{1} ግ ቀለም ያዘ፡ ነካ፥ በቀለም ተነከረ።

ቀለም (ብ.ቁ.**ቀለማት**) ስ 1. ከእፅዋት ወይም ከአፈርና ከሌሎችም ልዩ ልዩ ነገሮች በፈሳሽ ወይም በዱቄትና በጭቃ መልክ የሚዘጋጅና ለማቅለሚያ ወይም ለመፃፊያ የሚያገለግል እንደ አረንጓዴ፥ቢጫ፥ ቀይ፥ ሰማያዊ፥ ጥቁር፥…ያለ መልክ ያለው ነገር። 2. መልክ። *የቤትዎ ቀለም ተበላሽቷል።* 3.አይነት። *ቀለሙ ነጭ ነው።* 4.(ዘይ.) ትምህርት። *ቀለም ይገባዋል።*

ቀለም አገባ በቀለም ነከረ።

ቀለም ይይዛል ትምህርት ይገባዋል።

ቀለም ገባው ትምህርት ገባው።

ቀለም ቀቢ ስ ስራው የቤት ግድግዳዎችን፥ በርና መስኮቶችን፥… ቀለም መቀባት የሆነ ሙያተኛ።

ቀለም ቅብ ስ በሸራ፥ በሰሌዳ፥ በወረቀት፥…ላይ በቀለም የሚሰራ የስእል ጥበብ።

የቀለም ልዩነት ስ ነጮች በጥቁሮች ላይ የሚያደርጉት የዘር መድልዎ።

የቀለም ሰው ስ 1. የትምህርት ወይም የእውቀት ሰው፥ ሊቅ፥ ምሁር። 2. ብሩህ አእምሮ ያለው፡ ትምህርት የሚገባው ሰው።

የቀለም ቀንድ ስ 1. ቀለም የሚበጠበጥበትና የሚቀመጥበት ከቀንድ የተሰራ የቀለም መያዣ። 2. (ዘይ.) ምሁር፥ ሊቅ።

የቀለም ትምህርት ስ ሙያ ነክ ያልሆነ ትምህርት።

የቀለም አባት ስ አስተማሪ፡ መምህር።

ቀለማም ቅ ቀለሙ ደማቅ የሆነ።

አቀለመ ግ ቀለም አገባ ወይም ቀለም ውስጥ ነከረ።

ቀለመ^{2} "**ቀለበ**^{2}"ን ተመ.

***ቀለመ**

ቀለም ስ ቀሰም፡ ቀጭን መቃ።

ተቀለመ ግ ተጸወረ።

አቀለመ ግ አጸወረ፥ አጠነጠነ፡ በቀሰም ላይ ፈትልን ጠቀለለ።

አቅላሚ ስ አዳዋሪ።

ቀለማም "**ቀለመ**^{1}" ስር ተመ.

ቀለም^{1} "**ቀለመ**^{1}" ስር ተመ.

ቀለም^{2} "***ቀለመ**" ስር ተመ.

ቀለሰ ግ 1. አጎበጠ፥ አስጎነበሰ። 2. በአሂዶ ጊዜ ቀላሹ በሬ አሆረ፥ አሟረ፡ ሌሎቹ ከብቶች እሱን እየተከተሉ ክብ በመዞር ነዶውን እንዲረግጡ መራ።

ቀላሽ ስ አሟሪ፥ ፊት መሪ በሬ (በአሂዶ ጊዜ)።

***ቀለሰለሰ**

ቅልስልስ(ቀለስላሳ) ቅ 1.ደካማ፥ ዝልፍልፍ፥ ልፍስፍስ። 2. አይነአፋር፥ ተሽኮርማሚ።

ተቅለሰለሰ ግ 1. ደከመ፥ ተዝለፈለፈ፡ ተልፈሰፈሰ። 2. እንደማፈር፥ እንደመሽኮርመም አለ።

አቅለሰለሰ ግ 1. አደከመ፥ አዝለፈለፈ፥ አልፈሰፈሰ። 2. በመሽኮርመም፥ በማፈር አይነት ራሱን ዘንበል ቀና አደረገ።

***ቀለሸለሸ**

ቅልሽልሽታ ስ ማጥወልወል።

ቅልሽልሽ አለ ግ 1. አጥወለወለ፥ ልውጣ ልውጣ አለ (ትውከት)። 2. (ዘይ.) ሰለቸ፥ አንገፈገፈ።

አቅለሸለሸ ግ 1. አጥወለወለ፡ ልውጣ ልውጣ አለ (ትውከት)። 2. (ዘይ.) ሰለቸ፡ አንገፈገፈ።

*ቀለቀለ

ቅልቃላ (ቀለቀል) ቅ ቀዥቃዣ፥ ክውካዋ፥ ቀውቃዋ።

ቅልቅል አለ ግ ተንቀለቀለ፥ ተንቀዠቀዠ፥ ተንከወከወ፥ ተንቀወቀወ።

ቅልቅል አደረገ ግ አንቀለቀለ፤ አንቀዠቀዠ፤ አንከወከወ፤ አንቀወቀወ።

ንቅልቃል ስ የእሳት ወላፈን፥ ነበልባል።

ተንቀለቀለ ግ 1. ተንቀዠቀዠ፤ ተንከወከወ፤ ተንቀወቀወ። 2. ተንበለበለ፥ ተንቦገቦገ፥ በሃይል ነደደ (እሳት)።

አንቀለቀለ ግ 1.አንቀዠቀዠ፤ አንከወከወ፤ አንቀወቀወ። 2. አንበለበለ፥ አንቦገቦገ (እሳትን)።

ቀለቀንዳ (ቃለቀንዳ) (ስድብ) ቅ 1. ለፈኛ፥ ነገረኛ፥ ለፍላፊ። 2. አሳባቂ።

ቀለበ[1] ግ 1. አዘውትሮ ምግብንና መጠጥን እያዘጋጀ ለተቀላቢ መገበ፤ አበላ። 2. እየመገበ አወፈረ፥ አደለበ (ሙክትን፥ ሰንጋን፥...)።

ቀለብ ስ 1. በየጊዜው እየተዘጋጀ ለተጠቃሚው የሚቀርብ ምግብና መጠጥ። 2. ለተወሰነ ጊዜ የሚበቃ እህል፥ የምግብ ፍጆታ። 3. በተወሰነ ጊዜ የሚከፈል የአገልግሎት ዋጋ፤ ደመወዝ።

ቀለብ ሰፈረ ቀለብ ሰጠ (በወር፥ በአመት፥...)።

ቀለብተኛ ስ 1. ከአንድ ግለሰብ፥... ዘንድ ምግብን፥ መጠጥን፥ ....እያገኘ የሚኖር ጥገኛ፥ ተረጂ፥ በላተኛ ሰው። 2. ስ ከአንድ ግለሰብ፥ ቤተሰብ፥...ጋር ባለው የስራ ወይም የሌላ ነገር ግንኙነት ምክንያት በተወሰነ ጊዜ የተወሰነ ገንዘብ፥ እህል፥... የሚሰጠው ወይም የሚከፈለው ደመወዝተኛ።

ቀላቢ ስ ምግብና መጠጥን እያዘጋጀ ገንዘብ በማስከፈል ወይም በነፃ በቋሚነት ተቀላቢውን የሚያበላና፥ የሚያጠጣ።

ቅልብ ቅ ወፍራም፥ ድልብ።

ተቀለበ ግ በተወሰነ ቦታ በቋሚነት ተመገበ፥ በላ። 2. በሚገባ እንዲመገብ ተደረገ፥ ወፈረ፥ ደለበ።

ተቀላቢ ስ በአንድ በተወሰነ ቦታ በቋሚነት የሚበላ ተመጋቢ፥ የምግብ ደንበኛ።

ቀለበ[2] **(ቀለመ)** ግ የተወረወረን ነገር ምድር ሳይነካ ያዘ፥ በእጁ አደረገ።

ቅልቦሽ (ቅልሞሽ) ስ ልቅሞሽ።

ቅልልቦሽ (ቅልልሞሽ) ስ ልጆች ኳስን ምድር ላይ እያነጠሩ በመቅለብ የሚጫወቱት ጨዋታ።

*ቀለበለበ

ቅልብልብ(ቀለብላባ) ቅ 1. ችኩል፥ ክላባ፥ ክልብልብ። 2. ምላሰኛ።

ቅልብልብ አለ ግ ተቅለበለበ።

ተቅለበለበ ግ ቸኮለ፥ ተክለበለበ፥ ተጣደፈ። 2. አፈቸለ፥ ቀባጠረ።

አቅለበለበ ግ 1. አስገበገበ፥ አስቸኮለ፤ አክለበለበ፥ አጣደፈ።2. አስቀባጠረ፥ አናገረ።

ቀለበሰ ግ 1. ወደ ውስጥ ወይም ወደ ውጪ አጠፈ፥ ገለበጠ፥ ቀነፈ (የጨርቅንና የመሳሰለውን ጫፍ)። 2. ወደ ኋላ መለሰ። *ጓዴን ቀልብሶ መጣ።*

ቀልባሽ ቅ አደሃሪ፥ ጎታች፥ አደናቃፊ።

ቅልበሳ ስ የአንድን አዲስ ስርአተ ማህበር እርምጃ ለማጨናገፍ የሚደረግ እንቅስቃሴ።

ቅልብሳት ስ እጥፋት፥ ቅንፋት።

ተቀለበሰ ግ ወደኋላ ተመለሰ።

*ቀለበሰ

ተንቀላበሰ ግ አልብሱኝ፥ አንተርሱኝ፥ አንሱኝ ደግፉኝ አለ (በድሎት፥ በመቀማጠል ወይም በህመም ምክንያት)።

አንቀላበሰ ግ ተንከባከበ፥ በጥንቃቄ ያዘ።

ቀለበት ስ 1. ከብር ወይም ከወርቅ ወይም ከነሃስ፥...የሚሰራ ክብና ክፍት የሆነ የጣት ጌጥ። 2. ማንኛውም ዙሪያ ክብነት ያለው ውስጡ ክፍት ነገር። 3. የጋብቻ ውል መፈራረሚያ ቀን፥ ፍጥምጥም።

ቀለበት አሰረ 1. የጋብቻ ቃልኪዳን ምልክት የሆነውን ቀለበት አደረገ። 2. የጋብቻ ውል ተፈራረመ።

ቀለበት አደረገ ቀለበት አሰረ።

ቀለበት ውስጥ ገባ በማያመልጥበት፥ መፈናፈኛ በማያገኝበት ሁኔታ ውስጥ ገባ።

የቀለበት ጣት ስ በትንሽ ጣትና በመሃል ጣት መካከል የሚገኝ (የቃል ኪዳን ወይም የጋብቻ ቀለበት የሚደረግበት) የግራ እጅ ጣት።

*ቀለበጨ

ቀልባጫ ቅ 1. እጥር ምጥን ያለ። 2. ቀልጣፋ።

ቅልብጭ (ቀልበጭ) ያለ ዝ.ክ.

ቀለብ "ቀለበ[1]" ስር ተመ.

ቀለብላባ "*ቀለበለበ" ስር "ቅልብልብ"ን ተመ.

ቀለብተኛ "ቀለበ[1]"ስር ተመ.

ቀለተ ግ ረዳ፥ አገዘ፥ ረጠበ (ለተቸገረ፥ ንብረት ለጠፋበት፥ እዳ ለገባ፥...)።

ቀለታ(ቀለት) ስ እርጥባን፥ እርዳታ።

ቀለንጆ (ቀሌንጆ) ስ መጠኑ ትንሽ የሆነ የዝሆን ጥርስ።

*ቀለወ

ቀላዋ ቅ ከሳባ፣ ከሳፋ፣ ቀዥቃዣ።

ቀለው ቀለው አለ ግ ተንቀዠቀዠ።

ቀለዋ (ቀላዎ) ስ ፍሬው የእከክ መድሃኒት ነው የሚባል መጠኑ አነስተኛ የሆነ የዛፍ አይነት።

ቀለደ ግ 1. አባለተ፣ ተረበ፤ ዋዛ ፈዛዛ ተናገረ። 2. አሳገጠ፣ አሾፈ፣ አፌዘ። *በስራ ይቀልዳል።*

ቀላጅ ቅ 1. አባላች፣ ተራቢ። 2. አሳጋጭ፣ አሿፊ። 3. ተጫዋች፣ ጨዋተኛ።

ቀልድ ስ 1. ቧልት፣ ተረብ፣ ፌዝ፣ ጨዋታ። 2. ውሸት፣ የምር ያልሆነ ነገር።

የቀልድ የእውነት፣ የምር ያልሆነ።

ቀልደኛ ቅ 1. ቧልተኛ፣ ተረበኛ፤ ፌዘኛ፣ ተጫዋች። 2. አላጋጭ፣ አሿፊ።

ተቀለደ ግ ተላገጠ፤ ተሾፈ፣ ተፌዘ።

ተቀላለደ ግ በቀልድ ተጫወተ።

ተቃለደ ዝ.ከ.

ተቃላጅ ቅ ቀልደኛ፤ ተጫዋች።

አቃለደ ግ አዋዛ፣ አጫወተ። *እያቃለደ ስራውን አዘናጋኝ።*

ቀለጠ ግ 1. ሟሟ፣ ወደ ፈሳሽነት ተለወጠ (ከሙቀት የተነሳ)። 2. ደራ፣ ደመቀ፣ ሞቀ (ዘፈኑ፣ እልልታው፣...)። 3. ተሸበረ፣ ተደበላለቀ (እሪታ፣ ጩሀት፤ ኡኡታ፣...)። 4.(ዘይ.) ዘ.ጠፋ። *ገንዘቤ ቀለጠ።* ሲከሰረ። 5. ተመታ፣ ተደበደበ። *ሌባው በዱላ ቀለጠ።* 6.ወፈረ፣ ደነደነ፣ ሰባ፣ ሎማ ሆነ። *ሙክቱ ቀለጠ።* 7.ተናደ፣ ፈረሰ፣ ወደቀ። *ዝናብ ስለበዛበት ከረብታው ቀለጠ።* 8. ከህመም፣ ከከባድ ስራ፣... የተነሳ ደከመ፣ ተዝለፈለፈ። 9 . ተሞላቀቀ። *ልጅህ ቀልጧልና ስነስርአት አስተምረው።*

ቀለጤ ቅ ቅብጠት የሚያበዛ፣ ሞልቃቃ (ለልጅ)።

ቅልጣን ስ 1. ምቾት፣ ድሎት። 2. ቅብጠት፣ መሞላቀቅ።

ቅልጥልጥ ቅ ወዛም፣ ስብነት ያለው።

ቅልጥ አለ ግ 1. ሄዶ ቀረ፣ ጥፍት አለ። 2. ቀለጠ።

ቅልጥ ያለ 1. በጣም የደመቀ። *ቅልጥ ያለ ከተማ።* 2. በጣም የሰባ። *ቅልጥ ያለ ሰንጋ።* 3. በጣም የተሞላቀቀ። *ቅልጥ ያለ ልጅ።*

ተቃለጠ ግ ተማታ፣ ተደባደበ (እርስ በእርስ)። *ጎረምሶች በዱላ ተቃለጡ።*

ተቅለጠለጠ ግ 1. ወዛ፣ ቅባት የተቀባ መሰለ። 2. ሰባ፣ ሎማ ሆነ።

አቃለጠ ግ 1. አዳመቀ። 2. አጫረሰ (ሃብትን አብሮ በማባከን)።

አቃልጣ ቅ ወሬ አዳማቂ።

አቅልጥ (አቅላጭ) ቅ አክሳሪ።

አቅለጠለጠ ግ አወዛ፣ ቅባት የተቀባ አስመሰለ።

አቅለጥልጥ ቅ አቃልጣ።

ቀለጠመ ግ መታ፣ ሰበረ፤ አነከተ (ለምሳሌ እጅን፣ እግርን)።

ቀልጣማ ቅ በቀላሉ የሚሰበር፣ አቅመ ቢስ።

ቅልጥም ስ 1. ከጉልበት እስከ ጫማ ያለው የእግር ክፍል(ስእሉን ሰውነት ስር ተመ.)። 2. በሁለት አንጓዎች መካከል የሚገኝ፣ በውስጡ ቅባት ወይም መቅኒ የሚይዝ፣ መስል ያለ ውስጡ ክፍት አጥንት። 3. በሁለት አንጓዎች መካከል የሚገኝ መሰል ያለ አካል። *የሸንኮራ አገዳ ቅልጥም።* 4. ከቅልጥም አጥንት ውስጥ የሚገኝ ቅባት፣ መቅን ወይም መቅኒ።

ቅልጥሙ ፈሰሰ ዛለ፣ ደከመ፣ ተብረከረከ።

ቅልጥም አለ ግ እንክት አለ፣ ተሰበረ።

ቅልጥም አወጣ 1. አደገ፤ በረታ፣ ጎለበተ። 2. አደገ፣ እንጓ ለየ፣ አበጀ (የአገዳ እህል)።

ቅልጥማም ቅ ረጋርጃም ቅልጥም ያለው።

ቀለጣጠመ ግ ሰባበረ።

ተቀለጠመ ግ ተሰበረ።

ተቀለጣጠመ ግ ተሰባበረ።

*ቀለጠጠ

ቀልጣጣ (ቀለጠጥ) ቅ 1. ግልጥ ወይም ከለላ አልባ የሆነ (ቦታ)። 2. በልማጣ፣ አይኑ የሚንቀዠቀዥ፣ ሃፍረተ ቢስ።

ቅልጥጥ ዝ.ከ.

ቅልጥጥ አለ ግ 1. ግልጥ አለ፣ ወለል ብሎ ታየ፣ ከለላ አልባ ሆነ። 2. ተንበላጠጠ፣ አይኑ ተንቀገረቀገ።

ቅልጥጥ አደረገ ግ ገለጠጠ፤ ወለል፣ ግልጥ አድርጎ አሳየ።

ተንቀለጠጠ ግ 1. ተከፈተ፣ ተገለጠ፣ ወለል ብሎ ታየ። 2. ሃፍረተ ቢስ ሆነ። 3. ተንገለጠጠ፣ ተንተረከከ፣ ጋመ (ፍም)።

ቀለጠፈ ግ 1.በፍጥነት፣ በቶሎ ተከናወነ፣ ተደረገ፣ ተሰራ። 2. ፈጠነ።

ቀልጣፋ ቅ አንድን ነገር በፍጥነት መስራት የሚችል፤ ፈጣን።

ቅልጥፍና ስ በፍጥነት የመስራት ችሎታ፤ ፍጥነት።

ቅልጥፍጥፍ ያለ ዝርክርክ ያልሆነ፣ ጥንቅቅ

ስብስብ ያለ።

ተቀላጠፈ ግ 1. በፍጥነት ተከናወነ። 2. በፍጥነት አከናወነ።

ተቀለጣጠፈ ዝ.ከ.

አቀላጠፈ ግ በፍጥነት አከናወነ፤ ቶሎ ፈፀመ፥ ሰራ።

አቀላጥፎ ይናገራል በደንብ፥ በትክክል ይናገራል። *አማርኛ አቀላጥፎ ይናገራል።*

ቀለጤ "ቀለጠ" ስር ተመ.

ቀላ^{1} ግ 1. ቀይ ሆነ። 2. በሰለ፥ ጎመራ (ለፍራፍሬ)።

ቀያቴ ቅ ቀይነት ያለው (ለአፈር)።

ቀይ(ብ.ቁ.ቀያይ) ቅ 1.ግምጃ፥ በርበሬ፥ ደም የሚመስል። ስ 2. ከጠይም ፈካ የሚል የሰው መልክ። 3. በርበሬ፥ ደም፥...የሚመስል ቀለም።

ቀይ መስቀል ስ የጦርነት ወይም የተፈጥሮ አደጋ ባጋጠመበት ቦታ ፈጥኖ እየተገኘ ጉዳት ለደረሰባቸው ሁሉ አስፈላጊውን ሰብአዊ እርዳታ የሚያደርግ አለማቀፋዊ የእርዳታ ድርጅት።

ቀይ ስር ስ ደም የሚመስል ቀለም ያለውና ስሩ እንደድንች ያለ የሚበላ ተክል።

ቀይ ስር

ቀይ ሽብር ስ በሶሻሊስት ስርአተ ማህበር ውስጥ የስርአቱ አራማጆች፥ ፀረ አብዮተኞች ናቸው በሚሏቸው ላይ የሚያካሂዱት የግድያ ተግባር።

ቀይ ሽንኩርት ስ ቅርፁ ክብ ሆኖ እንደ ድንች በመሬት ውስጥ የሚያድግ፤ የተነባበረ ልጣጭ ያለው፥ ለምግብ ማጣፈጫነት የሚያገለግል ተክል።

ቀይ አፈር ስ ቀይነት ያለው አፈር፥ ቦረቦር።

ቀይ ወጥ ስ በርበሬ የገባበት ወጥ።

ቀይ ዳማ ስ ቀለሙ በጠይምና በቀይ መካከል የሆነ የሰው መልክ።

የቀይ ጥቁር ሆነ ቀይ የነበረው በጉስቁልና ምክንያት ጠቆረ።

የቀይ ጥቁር ነው መልኩ እንደ መልአክ ቀይ ቢሆንም ክፉ፥ ተንኮለኛ ነው።

ቅላት ስ ቀይነት፥ ግምጃ መልክ።

ቀላ^{2} ግ መታ፥ ለጋ (እሩሩን፥ ጥንግን፥ ኳስን፥...)።

ቅሌ ስ እሩር፥ ጥንግ።

ቀላ^{3} ግ ቆረጠ። *አንገቱን በጎራዴ ቀላው።*

ቀላል "ቀለለ" ስር ተመ.

ቀላመደ ግ ዘላበደ፥ ቀላፈተ፥ ዘባረቀ፤ የሆነ ያልሆነውን ቀባጠረ፤ ውሸትና እውነትን ቀላቅሎ ተናገረ።

ቀልማዳ(ቀላማጅ) ቅ 1. ዋሾ፥ ወሽካታ፥ ቀላፋች። 2. ዘባራቂ፥ ዘላባጅ።

አስቀላመደ (አቀላመደ) ግ 1. አስዋሸ፥ አስቀላፈተ፤ አስቀባጠረ። *ምን ያስቀላምድሃል።* 2. አስዘላበደ፥ የሆነ ያልሆነውን አስቀባጠረ።

ቀላሸ "ቀለሰ" ስር ተመ.

ቀላቀለ ግ 1. ቀየጠ፥ ዘነቀ። 2. አገናኘ፥ ደባለቀ።

ቅልቅል ቅ 1.ድብልቅ፥ ቅይጥ። ስ 2. አልኮለኝነት ያለው የመጠጥ አይነት። 3. የወንዱና የሴቷ ሙሽራ ቤተሰቦች ሙሽራው ቤት በአንድነት ተገናኝተው ራት የሚጋበዙበትና የሚተዋወቁበት ቀን።

ተቀላቀለ ግ 1. ተደባለቀ፥ ተቀየጠ። 2.ገባ፥ አብሮ ሆነ፥ ተደባለቀ።

አቀላቀለ ግ 1. አገናኘ (ዘመድ ከዘመድ)። 2. (ነውር) ዘመዳሞችን በወሲብ ተገናኘ።

ቀላቢ "ቀለበ^{1}" ስር ተመ.

ቀላባ ቅ ከላባ፥ ቀለብላባ።

ቀላወጠ ግ 1. ሳይጠራ፥ ሳይጋበዝ፥ ሳይፈለግ በየቤቱ እየሄደ በላ፥ ጠጣ። 2. ለመነ፥ ቀፈፈ፥ ሂገተ። 3. ከጀለ፥ ፈለገ፥ ሻ፥ ጓጓ። *አይኑ ቀላወጠ።*

ቀላዋጭ ስ ሳይጠሩት፥ ሳይጋብዙት፥ ሳይፈልጉት በየቤቱ እየዞረ የሚበላ፥ የሚጠጣ።

ቅልውጥ ስ 1.ባልተጋበዙበት፥ ባልተፈለጉበት ቦታ እየተገኙ የመብላትና የመጠጣት ድርጊት። 2. ልመና፥ ቀፈፋ።

አቀላወጠ ግ ለቀላዋጭ ሰጠ፥ አበላ።

ቀላዋ ""ቀለወ" ስር ተመ.

ቀላዎ "ቀላዋ" ን ተመ.

ቀላይ (ብ.ቁ..ቀላያት) ስ ጥልቅና ሰፊ የሆነ ባህር፥ ውቅያኖስ።

ቀላድ ስ 1. ርዝመቱ 150 ክንድ ሆኖ ከቆዳ ወይም ከእንሰት ወይም ከጭረት፥... የተሰራ ገመድ፥ ወደሮ። 2. በቀላድ የተለካ፥ የተሰፈረ መሬት።

ቀላድ ወደቀ/ተጣለ በቀላድ ተለካ፥ ተሰፈረ

(መሬት፥ እርስት)።

ቀላድ ጣለ 1. መሬትን በቀላድ ለካ፥ ሰፈረ። 2. በቀላድ እየለካ ሰጠ(መሬትን)።

ቀላድ ጣይ ስ መሬትን በቀላድ እየለካ ለታዘዘለት ሰው ይሰጥ የነበረ የመንግስት ሰራተኛ።

ቀላጅ "ቀለደ" ስር ተመ.

ቀላጤ (ቃለአጤ) ስ 1. አቤት ባይ ወይም ተበዳይ ከበላይ አካል የሚያመጣው የውሳኔ ማጽኛ ወይም ማፍረሻ ትእዛዝ። 2. የንጉስን ወይም የባለስልጣንን ትእዛዝ በቃል ተቀብሎ በቃል ለሚመለከተው ወገን ያደርስ የነበረ መልእክተኛ።

ቀላጥም ስ የቃሬዛ፥ የመሰላል፥...አግዳሚ እንጨት።

ቀላጥቤ "ቅላጥቤ" ን ተመ.

ቀሌንጅ "ቀለንጅ" ን ተመ.

ቀልማዳ "ቀላመደ" ስር ተመ.

ቀልቀሎ ስ ስልቻ።

ቀልቃላ "*ቀለቀለ" ስር ተመ.

ቀልበቢስ "ቀልብ" ስር ተመ.

ቀልባሻ "ቀለበሰ" ስር ተመ.

ቀልባጫ "ቀለበጨ" ስር ተመ.

ቀልቤ ስ ከሽፋል በላይ በግንባር ዙሪያ በቀጭን ታስሮ ጫፍና ጫፉ በማጅራት በኩል የሚወርድ ሻሽ።

ቀልብ ስ ማስተዋል፥ ማስታወስ የሚያስችል አእምሮ፤ ልብ።

ቀልቡ ጠፋ 1. ረሳ፤ ዘነጋ (አንድን ነገር ማድረግ፥ መፈፀም፥...ን)። 2. ማስተዋል ተሳነው፤ ልቡ ጠፋ።

ቀልብ ገዛ አስተዋይ ሆነ፤ ጠመተ።

ቀልበ ቢስ ቅ 1. ልበ ቢስ፥ ዝንጉ፥ ቶሎ የሚረሳ። 2. ጥላ ቢስ፥ ከውካዋ።

ቀልበ ደረቅ ለዛ ቢስ።

ቀልደኛ "ቀለደ" ስር ተመ.

ቀልድ ዝ.ክ.

ቀልጣማ "ቀለጠመ" ስር ተመ.

ቀልጣጣ "*ቀለጠጠ" ስር ተመ.

ቀልጣፋ "ቀለጠፈ" ስር ተመ.

ቀመለ ግ 1. ቅማልን ለቀመ፥ አነሳ፤ ገደለ። 2. ቅማል፥ አፈራ።

ቅማል ስ በሰው ልብስና በፀጉር ንፅህና ጉድለት ምክንያት የሚፈጠርና ደም እየመጠጠ የሚኖር ጥቁር ወይም ነጭ ተባይ።

ቅማል

ቅማላም ቅ 1. (ስድብ) ዘወትር ቅማል የማይለየው። 2- (ዘይቤስድብ) ምንም ሃብት የሌለው፥ ችግረኛ። *ቅማላም ድሃ።*

ቀመመ ግ ልዩ ልዩ ነገሮችን መጥኖ በመደባለቅና በማዋሃድ እንደመድሃኒት፥ መርዝ፥ ቅመም፥...ያሉትን አዘጋጀ።

ቀማሚ ቅ 1. መድሃኒትን፥ መርዝን፥ ቅመምን፥...የሚያዘጋጅ። 2. የቅመማ ተግባር ባለሙያ።

ቅመማ ስ ቅመም የማዘጋጀት ተግባር።

ቅመም ስ 1. ከተለያዩ ተክሎች ፍሬ-ፍሬ ወይም ስራስር ወይም ቅርፊት፥... የሚዘጋጅና ለምግብ ማጣፈጫነት የሚያገለግል እንደ ነጭና ጥቁር አዝሙድ፥ ጅንጅብል፥ ሽንኩርት፥ ቀረፋ ያለ ነገር። 2. አንድን ነገር ለመስራት አስፈላጊ የሆነ ንጥረ ነገር። *መድሃኒቱን ለመስራት አስፈላጊ የሆኑት ቅመሞች ተዘጋጅተዋል።* 3. (ዘይ.) ባለሙያ። *ልጅቷ ቅመም ናት።*

ቅመማ ቅመም ስ የተለያዩ የቅመም አይነቶች።

ቅምም ቅ በቅመም የተዘጋጀ፥ የተከሸነ፥ የተቀመመ።

ቀመረ ግ 1. ቆጠረ። 2. አዘጋጀ፥ አከናወነ።

ቀመር ስ ቁጥር፥ ስሌት።

ቀመር¹ ስ ፍሬው ትንንሽ የሆነ አደንጓሬ።

ቀመር² ስ ዋልታ፤ የቤት ግብታ።

ቀመር³ "ቀመረ" ስር ተመ.

ቀመሰ ግ 1. በጥቂቱ በላ፥ ጠጣ፥ ለከፈ። 2. ጣእሙን ለማወቅ በጥቂቱ ጎረሰ፥ ቶት አለ፥ ላሰ። 3. አየ፥ ተቀበለ (ችግርን፥ መከራን፥...)። 4. (ዘይ.) ሀ ከዚህ በፊት ተገናኝቷት የማያውቃትን ሴት ለመጀመሪያ ጊዜ በግብረ ስጋ ተገናኘ። ለ ተመታ፥ ተደበደበ። *ዱላ ቀመሰ።*

-ቀመስ -ነክ፤ በትንሹ ያለበት ወይም ከ-ጋር ግንኙነት ያለው። *ታሪክ ቀመስ/ አሸዋ ቀመስ/ ከተማ ቀመስ።*

ቀማሽ ቅ በቤተ መንግስት ይደረግ በነበረ ግብዣ ላይ፥ የተዘጋጀው ምግብ ለንጉሱ ወይም ለተጋባዡ ከመቅረቡ በፊት ምግቡና መጠጡ ደረጃውን የጠበቀና ተስማሚ መሆኑን በመቅመስ ይቆጣጠር የነበረ ባለሟል።

ቅምሻ ስ አነስተኛ ምግብ ወይም መጠጥ፤ ለመቅመስ ያህል የቀረበ።

ተቀማመሰ ግ 1. በጥቂቱ ተከፋፈለ፥ ተቋደሰ። 2. ተደባደበ፤ ተማታ (አንዱ ከሌላው ጋር)።

ተቃመሰ ግ ተቀማመሰ።

አቀመሰ ግ 1. መታ። 2. አዋጣ፥ አበላ፥

አጠጣ፤ (መድሃኒትን)።3. በትንሹ አበላ፥ አጠጣ፥...።

ኢያቀምስም (ኢያስቀምስም) ምንም አይሰጥም።

አቀማመሰ ግ ለዚህም ለዚያም በትንሽ በትንሹ አቀመሰ፤ አዳረሰ (ለምሳሌ ምግብን)።

ኢቃመሰ ዝ.ክ.

አላስቀምስ አለ ከለከለ፤ አልሰጥ፤ አላስነካ አለ።

አይቀመስም አይደፈርም፤ አይበገርም፤ አይነካም።

ቀመቀመ^{1} ግ 1. የልብስን ጠርዝ በትንሹ አጥፎ ወይም ሌላ ማፈኛ ክፈፍ አስገብቶ ዳር ዳሩን ለፋ፤ ዘመዘመ። 2. የልብስ ቁልፍ ማስገቢያ ቀዳዳዎችን ዙሪያ በክር ዘመዘመ።

ቅምቅማት ስ የልብስ ጠርዝ፤ ዝምዝማት።

ቀመቀመ^{2} ግ በትንሹ ጠጣ፤ በቀለ፤ ብቅ ብቅ አለ።

ቅምቀማ ስ በትንሹ የጠጣ፤ የበቀለ፤ ብቅ ብቅ ያለ ጠጉር።

አቀመቀመ ግ ፀጉር አወጣ፥ አበቀለ።

ቀመቀመ^{3} ግ ብዙ ጠጣ (የሚያሰክር መጠጥ)።

ቅምቃሚ ቅ አዘውትሮ የሚጠጣ፤ ጠጪ።

ቀመቀመ^{4} ግ ፀጉርን ፥ ብክልን፥...አስተካከለ፥ ቆረጠ።

ቅምቃሚ ስ ፀጉር አስተካካይ።

***ቀመቀመ**

ተቀማቀመ ግ ህፃን ልጅ ወይም ገመምተኛው ምግብ ለመብላት ሞከረ፥ ጣረ።

አቀማቀመ ግ ምግብ መብላት እንዲለምድ ገፋፋ፥ ረዳ (ህፃኑን፥ በሽተኛን)።

***ቀመደመደ**

ቀመድማዳ (ቅምድምድ) ቅ ሽምድምድ፤ ዝልፍልፍ፥ አቅመቢስ፤ ጥምልምል።

ተቅመደመደ ግ አቅም አጣ፥ ተዝለፈለፈ፤ ተሽመደመደ።

አቅመደመደ ግ አሽመደመደ፤ አዝለፈለፈ፤ አጥመለመለ፥ አቅም አሳጣ።

***ቀመጠ**

ቅማጭ ስ ተቅማጥ።

ቅማጧም ቅ (ስድብ፥ ነውር) ተቅማጣም።

ቅምጥ ቅ 1. የተቀመጠ፤ ቁጭ ያለ ወይም የተደረገ። ስ 2. ቁጭታ፥ በቁም ያልሆነ። *ከቅምጥህ ሳትነሳ ላቀብለኝ።* 3. በአንድ ሰው ተወስና በውሽምነት የተቀመጠች ሴት፤ እቁባት።

ቅምጠሽ (ቅምጥምጥሽ) ስ ልጆች አንዱ በአንዱ ትከሻ ላይ እየተቀመጡ፥ ኳስ እየወረወሩና እየነጠሩ በመቀበል የሚጫወቱት ጨዋታ።

ተቀመጠ ግ 1. ቁጭ አለ። 2. ቁጭ ተደረገ። 3. ቆየ፤ ሰነበተ፤ ኖረ። *አዲስ አበባ ውስጥ ብዙ ጊዜ ተቀመጠ።* 4. ከበቅሎ፤ ከፈረስ፤ ጀርባ ላይ ቁጭ አለ። 5. አይነምድርን ተፀዳዳ።

ተቀማጭ ቅ 1. ቁጭ ያለ ወይም የሚል፤ የተቀመጠ። *ተቀማጭ ለልፈኛ።* 2. ነዋሪ። 3. ለልዩ ልዩ ጉዳዮች መጠባበቂያ እንዲሆን የሚጠራቀም ወይም የተቀመጠ (ገንዘብ)።

መቀመጫ ስ 1. ቁጭ የሚባልበት፥ ማረፊያ (ወንበር፤ በርጩማ፤ መደብ፥ ድንጋይ፥...)። 2. መኖሪያ (ቤት፤ አገር፤ ቦታ፤...)። 3. ቂጥ።

ተቅማጥ ስ 1. የሚያስቀምጥ፥ የሚያስቀዝን በሽታ። 2. ቀጭን አይነ ምድር፤ ቅዘን።

ተቅማጥ ነዳው (ነውር) በብዛት አስቀዘነው፤ አስቀመጠው።

ተቅማጣም ቅ (ስድብ፤ ዘይ.) ፈሪ።

አቀማመጥ ስ 1. አደራረር፤ ቦታ አያያዝ። *የእቃዎቹ አቀማመጥ አልተስተካከለም።* 2. አኗኗር። *ከዚህ አገር አቀማመጥህ እንዴት ነው?* 3. የተፈጥሮ ሁኔታ (የመሬት፤ የአገር፤ የከተማ፤...)። *የቦታው አቀማመጥ ለእርሻ አይሆንም።*

አስቀመጠ ግ 1. ቁጭ አደረገ፤ ደፋ፤ ጠብቆ አቆየ፤ አኖረ (እቃን)። 2. ቁጭ አደረገ። 3. ቁጭ አሰኘ፥ ቁጭ እንዲል አደረገ። 4. አኖረ፤ መኖሪያ ሰጠ (ለሰው)። *ወንድሜ ከቤቱ አስቀምጦኝ ነበር።* 5. መቀመጫ ቦታ ሰጠ። *እንግዳውን አስቀምጧቸው።* 6. ቦታው በቂ ሆነ (ለሚቀመጠው ነገር)። *ይሄ ቦታ ቁምሳጥኑን ሊያስቀምጠው ይችላል።* 7. አጠራቀመ፤ ተቀማጭ አደረገ(ገንዘብን)። 8. እቁባት ያዘ፤ አኖረ።9. አስቀዘነ (መድሃኒቱ፤ በሽታው፤...)።

አላስቀምጥ አለው አስቸገረው፥ ነተነተው፤ ፋታ ነሳው።

ቀመጠለ ግ 1. ጎመደ፥ ጎረደ፥ ቀነጠሰ፤ ቆረጠ። 2. ገመደለ፥ ቆረሰ፥ ከፈለ። 3. አሳነሰ፥ አጎደለ፥ ከተገመተው በታች ዝቅ አደረገ።

ቅምጥል አለ ግ 1. የታሰበውን ያህል ሳይሆን ቀረ፥ በረከት አጣ። *ምርቱ ቅምጥል አለ።*

ተቀመጠለ ግ አነሰ፥ ጎደለ፥ ከተገመተው በታች ዝቅ አለ። 2. ተጎመደ፥ ተቀነጠሰ፥ ተቆረሰ።

ተቀመጣጠለ ግ ተቆራረሰ።

ቀመጠል "***ቀማጠለ**" ስር "**ቅምጥል**" ን ተመ.

ቀሚስ ስ 1. ቁመቱ እስከተረከዝ ሊደርስ የሚችል፥ የአንገትና የእጅ ማስገቢያ ያለው

ወይም ልቅ የሴቶች ልብስ። 2. ርዝመቱ እስከ ቁርጭምጭሚት የሚደርስ፥ ጎኑ ሰፊ የሆነ፣ በእጀጠባብ ቅርፅ የተዘጋጀ የክህናት ልብስ። 3. ፈረስና በቅሎ ከተጫኑ በኋላ ኮርቻውንና አካላቸውን በረዥሙ የሚሸፍን የወግ ልብስ። 4. የመሶብ ልብስ፣ መሸፈኛ። 5. በቀድሞ ጊዜ ባለስልጣን የሆኑ የቤተመንግስት ሰዎች የሚለብሱት የእጀጠባብ ቅርፅ ያለው የማእረግ ልብስ። 6. በቅዳሴ ጊዜ ከሌሎች ዲያቆናት ይልቅ ዋናውን የመሪነት ቦታ ይዞ የሚቀድሰው ዲያቆን (ገበሬ ሰናይ ዲያቆን)።

ቀማ ግ 1. በሃይል ወይም በጉልበት ወሰደ። 2. ነጠቀ፥ መንጠቀ (አንድን ነገር ከእጅ ላይ)። 3. ዘረፈ፥ ገፈፈ (ሃብትን፣ ንብረትን)።

ቀማኛ ስ ነጣቂ፣ ዘራፊ፥ ወንበዴ።

ቅሚያ ስ ዝርፊያ፣ ንጥቂያ፣ የውንብድና ተግባር።

ተቃማ ግ ተሻማ፣ ተናጠቀ።

አቃማ ግ አሻማ።

አስቀማ ግ በተንኮል ጉድለት፣ በንዝህላልነት አስወሰደ፣ አስነጠቀ።

ቀማሚ "**ቀመመ**" ስር ተመ.

ቀማሽ "**ቀመሰ**" ስር ተመ.

ቀማኛ "**ቀማ**" ስር ተመ.

***ቀማጠለ**

ቅምጥል(ቀምጣላ፣ ቀመጠል) ቅ 1. በድሎት፣ በምቾት፣ በእንክብካቤ የሚኖር። 2. ቀብራራ።

ተቀማጠለ ግ 1. በድሎት፣ በምቾት ተያዘ፥ በእንክብካቤ ኖረ። 2. ተሞላቀቀ፣ ተንቀባረረ።

አቀማጠለ ግ 1. በድሎት፥ በምቾት ያዘ፥ ተንከባከበ። 2. አሞላቀቀ፣ አንቀባረረ።

ቀምቀሞ "**ቀመቀመ**²" ስር ተመ.

ቀምቃሚ¹ "**ቀመቀመ**³" ስር ተመ.

ቀምቃሚ² "**ቀመቀመ**⁴" ስር ተመ.

ቀምበር "**ቀንበር**" ን ተመ.

ቀምበጥ "**ቀንበጥ**" ን ተመ.

ቀረ ግ 1. የመጣ ተቃራኒ፤ አልመጣም ለማለት ሲፈለግ የሚነገር። *ይመጣል የተባለው ሰው ቀረ።* 2. የሄደ ተቃራኒ፤ አልሄደም ለማለት ሲፈለግ የሚነገር። *ይሄዳል የተባለው ሰው ቀረ።* 3. ቆመ፥ ታገደ፥ ተሰረዘ፣ ተተወ፥ ተከለከለ። *ጤንነት ቀረ።* 4. ቆየ፥ ዘገየ። *ምነው ቀረህ ተቸሎና እንጂ* 5. ተረፈ። *ስንት ቀረህ?* 6. ጎደለ፥ አነሰ። *ስፍራው ሊሞላ ትንሽ ይቀረዋል።* 7. ዳነ ፥አመለጠ፣ ተረፈ። *ከሞት የሚቀር የለም።* 8. በዚያው ፀና፣ ረጋ። *አሜሪካ ሄዶ ቀረ።* 9. አለመሳካትን፥ አለመፈፀምን፥ አለመደረግን፤... ለመግለፅ የሚያገለግል ቃል። *ሳያይ ቀረ/ሳይሰማ ቀረ/ሳያገኝ ቀረ።* 10. አልተገኘም፥ ጠፋ። *ቀለበቱ ወድቆ ቀረ።*

ቀረበት አመለጠው (ጥሩ ነገር)።

በቀረ (በተቀረ፣ በስተቀር) አለበለዚያ። *ብታጠና ይሻልሃል በቀረ ትወድቃለህ።*

ከ__በስተቀር (በተቀር፣ በቀር) መዋ. 1. ከ ____ ሌላ፣ በላይ፥ በተረፈ። *ከዚህ በስተቀር ምንም አላገኘሁም።* 2. ሳይጨምር፣ ሲቀር። *ከአባትየው በስተቀር ሌሎቹ ሰምተዋል።*

የቀረው (የተቀረው) ሌላው። *ይህን ሰምቻለሁ፤ የቀረው ምንድን ነው?*

የቀረው ቢቀር ሌላው ተትቶ፣ ቢያንስ ቢያንስ። *የቀረው ቢቀር በሩ መዘጋትም አለበት።*

ይቅር አለ ምህረት አደረገ፣ ቅሬታውን፣ ቂሙን ተወ።

ይቅር ባይ መሃሪ።

ይቅር ተባባለ ታረቀ፣ ተስማማ።

ይቅርታ ስ 1.ቂም ወይም ቅሬታ እንዳይኖር፣ በዳይ ተበዳይን ምህረት የሚጠይቅበት የልመና ቃል። *ይቅርታ! ሳላይ ገፋሁህ።* 2. በደልን፣ ቂምን መተው፣ ይቅር ማለት፥ ምህረት ማድረግ። *ለእስረኞች ይቅርታ ተደረገላቸው።* 4. በንግግር መሃል ጣልቃ ገብቶ ለመናገርም ሆነ ጥያቄ ለመጠየቅ ሲፈለግ የአድማጭን ፈቃድ ማግኘት እንዲቻል በቅድሚያ የሚነገር የትህትና ቃል። *ይቅርታ! በጨዋታችሁ መካከል አንድ ነገር ልናገር።*

ይቅርታ አደረገ ማረ፣ ቅሬታውን፣ ቂሙን ተወ።

ቀሪ ቅ 1. የቀረ፣ ያልመጣ ወይም ያልሄደ። 2. ተራፊ። 3. ያለ፣ የሚኖር። *የሞተስ ሞተ ይብላኝ ለቀረው።*

ቅሪት ቅ 1. እርጉዝ፥ ነፍሰጡር፣ የፀነሰች (ሴት)። ስ 2. ርዝራዥ (ለምሳሌ ሃብት)።

ቅሪተ አካል ስ ጥንት ህይወት የነበራቸው፣ አሁን ግን ደርቀው በዘርስ ምድር ውስጥ የሚገኙ ጠጣር ነገሮች።

ቀሪት አለው/ብሎታል ገና ነው፣ እንደተፈለገው አልሆነም፣ መጠነኛ ጉድለት አለው (ለመልበስ፥ ለመድረስ፣ ለመሙላት፣...)።

ቅርት አለ ግ 1. በጣም ቆየ፥ ዘገየ። 2. ድንገት ትንፋሹ ተቋረጠ፣ ድብን አለ፣ ሞተ። 3.ዛለ፣ መራመድ አልችል አለ (እግር)። *እግሬ ወደፊት ቅርት አለብኝ።*

አስቀረ ግ 1. ወሰደ፣ ለራሱ አደረገ። 2. ከለከለ፣ ሳይመልስ ቀረ።3. እንዳይሄድ ወይም እንዳይመጣ አደረገ።

***ቀረመተ**

ቅርምት ስ የስጋ ክፍፍል፥ ቅርጫ።

ተቀረማመተ ግ 1. ተካፈለ፥ ተቃረጠ። 2. ተሻማ፥ ተቧጠቀ።

ተቀራመተ ዝ.ከ.

አቀራመተ ግ 1. አካፈለ፥ አቃረጠ። 2. አሻማ፥ አቧጨቀ።

ቀረረ ግ 1. ጠራ፥ ጠለለ። 2.አዘለ፥ ያዘ(አይኑ እንባን)። *እንባው ቀረረ።*

ቀረራ ስ ሊጥ ተቦክቶ ኩፍ ካለ በኋላ ከአናቱ ላይ ጠልሎ የሚታይና አርሾነት ያለው ኮምጣጣ ፈሳሽ።

ቅራሪ ስ 1. ቀረራ፥ የቀረረ፥ ጥላይ። 2. ጠላው ተጠጥቶ ወይም ተቀድቶ ካለቀ በኋላ አተላው ላይ ውሃ ተሞልቶ የሚገኘው መናኛ ጠላ፥ አሰር ውሃ።

ቀረር አደረገ ግ የጠራው፥ የጠለለው እንዳይደፈርስ ቀስ አድርጎ ቀዳ።

አቀረረ ግ 1. የጠራውን፥ የጠለለውን ቀስ አድርጎ ቀዳ። 2. አጠለለ፥ ውሃ ከላይ ያዘ፥ አዘለ። 3. ያዘ፥ ቋጠረ፥ አዘለ (አይን እንባን)።

አንቃረረ ግ 1. ከዚህም ከዚያም አጫለጠ፥ ጠጣ፥ አጠረቃቀመ (መጠጥን)። 2. አጥለለ፥ አቅረሮ ቀዳ።

እንቃራሪ ቅ ጠጪ፥ ሰካራም።

***ቀረረ**

ቀረርቶ (ቀረርቱ) ስ ሽለላ፥ የጦር፥ የጀግንነት ወኔ መቀስቀሻ ዜማ።

አቅራራ ግ ሸለለ፥ የጦር፥ የጀግንነት ወኔ መቀስቀሻ ዜማ አዜመ።

አቅራሪ ስ የጦር፥ የጀግንነት ወኔ መቀስቀሻ ዜማን የሚያዜም ሰው፥ ሸላይ።

አንቃረረ ግ ድምፁን ከፍ አድርጎ ጮሀ።

ቀረራ "**ቀረረ**" ስር ተመ.

ቀረርቱ "**ቀረረ**" ስር"**ቀረርቶ**"ን ተመ.

ቀረሮ (ቀራሮ) ስ እንጨቱ ጠንካራ የሆነና ለተለያዩ አገልግሎት የሚውል የዛፍ አይነት።

ቀረሸ ግ የጠባውን፥ የተጋተውን እንደማስታወክ አይነት ፍልቅ አደረገ (ህፃን ልጅ)።

ቅርሻት ስ በትውከት አምሳያ ሆኖ ከህፃን ልጅ ሆድ በመጠኑ ፍልቅ ብሎ የሚወጣ ፈሳሽ።

ቅርሻታም ቅ 1. ቅርሻት የሚበዛበት። 2. (ስድብ) በስካር ምክንያት ተገቢ ያልሆነ ንግግር የሚናገር፥ የሚሳደብ፥ ባለጌ።

አቀረሸ ግ ቀረሸ።

እስኪያቀረሸው እስኪያንገፈግፈው፥ እስኪሰለቸው። *እስኪያቀረሸው ነው የነገሩት።*

ቀረሸመ ግ 1.ከረሸመ፥ ቆረጠመ፥ ጎረደመ። 2. ሰበረ፥ አነከተ።

ቅርሽም አለ ግ እንክት፥ ስብር አለ።

ቀረሻሸመ ግ 1. ከረሻሸመ፥ ቆረጣጠመ፥ አደቀቀ። 2. ሰባበረ፥ አነካከተ።

ቅርሽምሽም አለ ግ ስብርብር አለ።

ቀረሻሽንቦ (ቀረሻሽምቦ) ስ እንደጉሎና እንደሸንበቆ ውስጡ ክፍት የሆነ፥ በቀላሉ የሚሰበር የእፅዋት አይነት፡

ቀረቀረ ግ 1. በርን ወይም መስኮትን እንዳይከፈት በመወርወሪያ፥ በመቀርቀሪያ ዘጋ፥ ሸጎረ፥ ከረቸመ። 2. አስገባ፥ ጨመረ፥ ደነጎረ፥ ከተተ። 3. ደበቀ፥ እማይታይ ቦታ አስቀመጠ፥ ሰወረ።

መቀራቅር(መቀራቅርት) ስ ለመውጣትና ለመግባት የሚያስቸግር ጠባብ ቦታ።

መቀርቀሪያ (ቅርቃር) ስ በርና መስኮት እንዳይከፈት የሚያግድ መሸንጎሪያ፥ ቅርቃር ወይም መወርወሪያ።

ቀርቀሬ ስ በጣም ጎድጓዳና ሸለቋማ የሆነ የቆላ መሬት።

ቀርቀር ስ ገደል።

ቅርቃር "**መቀርቀሪያ**" ን ተመ.

ቅርቅር አለ ግ ተቀረቀረ፥ ገብቶ ቀረ፥ ተወሸቀ።

ተቀረቀረ ግ ገብቶ ቀረ፥ አልወጣ አለ።

ቀረቀበ ግ 1. ሁለት ተመጣጣኝ ሸክምን (ጭነትን) በአህያ፥ በአጋሰስ፥... ጀርባ ግራና ቀኝ እንዲውል አድርጎ አሰረ፥ አቆራኘ፥ ወደነ። 2. እቃን፥ ልብስን፥...ሰበሰበ፥ ጠቅልሎ በአንድነት አሰረ። 3. (ዘይ.) በጣም እስኪጠግብ በላ።

መቀርቀቢያ ስ ቀርቃባን ለማሰር የሚያገለግል ጠፍር።

ቀርቃባ (ቅርቃብ) ስ 1. በአህያ፥ በአጋሰስ፥...ጀርባ ላይ ለመጫን እንዲያመች ተመጣጣኝ ሆኖ የታሰረ ወይም የተቆራኘ መንታ ጭነት፥ ሸክም።

***ቀረቀበ**

ቀርቀቦ ስ 1. ማንቀርቀቢያ፥ ሰፌድ። 2. "**ቀርበቦ**"ን ተመ.

ተንቀረቀበ ግ 1. ገርድፉ ከደቃቁ እንዲለይ ሆኖ በሰፌድና በመሳሰለው እቃ ተበጠረ፥ ተንገዋለለ። 2. ተናወጠ፥ ተንቀጠቀጠ፥ ራደ (ምድር፥...)። 3. ደጋግሞ ነጠረ (ኳስ እግር ላይ)።

አንቀረቀበ ግ 1. ገርድፉ ከደቃቁ እንዲለይ አድርጎ በሰፌድና በመሳሰለው አበጠረ፥ አንጠረጠረ፥ አንገዋለለ። 2. አናወጠ፥

አንቀጠቀጠ፡ አራደ (ምድርን፡...)።3. ደጋግሞ አነጠረ፥ ጢብ ጢብ አደረገ (ኳስን በእግር)።

ማንቀርቀቢያ ስ ለማንጠርጠር፡ ለማበጠር የሚያገለግል እቃ፥ ሰፌድ።

እንቅርቃቢ ስ ከተፈጨ ወይም ከተወቀጠ ነገር ውስጥ በሰፌድ ተንገዋሎ፥ ተንጠርጥሮና ተለይቶ የሚወጣው ያልደቀቀው ክፍል።

ቀረበ ግ 1. ተጠጋ፥ ቅርብ፥ አጠገብ ሆነ። 2. ደረሰ። *ዓመት በዓሉ ቀረበ።* 3. መጣ፡ በቦታው ላይ ተገኘ። *ወንጀለኛው ቀረበ፡* 4.ዝግጁ ሆነ፥ ተሰራ። *ገበታው ቀረበ፡* 5. ይበልጥ ተጠጋ፥ ተዛመደ፡ ተግባባ። *ከአንተ የቀረበ ጓደኛ የለኝም።* 6. ተነገረ፡ ተሰጠ፥ ተሰነዘረ። *ሃሳብ ቀረበ።*

ቀረቤታ ስ ቅርበት (የዝምድና፥ የወዳጅነት)።

ቅርብ ቅ 1. አጠገብ ያለ፥ የተጠጋ፥ ሩቅ ያልሆነ። 2. የጠበቀ፡ በጣም የተጠጋ (ለዝምድና፡ ለወዳጅነት)።

ቅርብ ለቅርብ የተጠጋጋ፥ ያልተራራቀ፥ አጠገብ ለአጠገብ ያለ።

[በ]ቅርብ ቀን በዚህ ሰሞን፥ በቅርቡ።

የቅርብ ሩቅ 1. ቅርብ ሆኖ የሩቅን ያህል የሚያደክም(መንገድ)። 2 አጠገብ ለአጠገብ ሆኖ የማይገናኝ፥ የማይጠያየቅ።

ቅርበት ስ 1. አጠገብነት። 2. የጠበቀ ግንኙነት (ለወዳጅነት፥ ለዝምድና)።

ተቀራረበ ግ 1. ተጠጋጋ፥ ቅርብ ለቅርብ ሆነ። 2. ተግባባ፥ ተስማማ። 3. ተመሳሰለ፥ ተመጣጠነ።

ተቀራራቢ ቅ ተመሳሳይ፥ ተመጣጣኝ።

ተቃረበ ግ 1. ተዳረሰ (ጊዜው)። 2. ተጠጋ፡ ወደ አካባቢው ቀረበ።

መቃረቢያ ስ 1. መዳረሻ። 2. ዋናው ቤተክርስቲያን እስኪሰራ ድረስ ለጊዜው እንደቤተክርስቲያን ሆኖ የሚያገለግል አነስተኛ ቤት፥ የታቦት ማረፊያ፥ መቃኞ።

አቀረበ ግ 1. አስጠጋ፥ አጠገብ አደረገ። 2. ቶሎ እንዲደርስ አደረገ፥ አሳጠረ (የቀጠሮ ጊዜውን) 3. አመጣ። 4. (ዝግጅቱን) ሰጠ፡ አበረከተ፥ አሳየ። 5. ዘመድ ወዳጅ አደረገ። 6. ሰጠ። *ሰላምታ አቀረበ።* 7. ሰነዘረ። *ወቀሳ አቀረበ።*

ማቅረቢያ ስ 1. ማምጫ፡ ማስቀመጫ፥ ማጓጓዣ(እቃ)። 2. ማባበያ፥ መማለጃ፥ ስጦታ፡...።

አቅራቢ ቅ ልዩ ልዩ ነገሮችን ወደሚያስፈልገው ቦታ የሚያቀርብ (ሰው፥ ድርጅት)።

አቅራቢያ ስ 1. በቅርብ ያለ ቦታ። 2. አካባቢ። *ሊነጋጋ አቅራቢያ እቦታው ደረስን።*

አቅርቦት ስ በተወሰነ ቦታና ጊዜ የተፈለገውን ሸቀጥ የማቅረብ አቅም።

አቀራረበ ግ አመጣ፡ አዘጋጀ፡ ደረደረ (የተለያዩ ነገሮችን)።

አቀራረበ ግ 1. አጠጋጋ። 2. ግንኙነት፡ ስምምነት እንዲፈጠር አደረገ፥ አግባባ።

*ቀረበበ

ቀርባባ(ቀረብባ) ቅ ከርፋፋ፡ ጎርባባ።

ቀርባባ ጆሮ ስ ትልቅ ጆሮ።

ተንቀረበበ ግ ተንከረፈፈ፡ ተንጎረበበ።

አንቀረበበ ግ አንከረፈፈ፡ አንጎረበበ።

ቀረባ ስ እሾሁንና የመሳሰለውን ቆንጥጦ ለመንቀል የሚያስችል መቆንጠጫ፡ ወረንጦ።

ቀረቤታ "ቀረበ" ስር ተመ.

ቀረቦ "ቀርበቦ" ን ተመ.

*ቀረነ

ቅራኔ ስ 1. አለመስማማት፡ አለመግባባት፡ ቅዋሜ። 2. ጥል፥ ግጭት።

ተቃረነ ግ 1.ተቃወመ፡ አልስማማ አለ። 2. እርስ በእርስ ተጣላ፥ ተጋጨ።

ተቃራኒ ቅ 1. ተፃራሪ፥ አፍራሽ። 2. ጠላት፥ ተቃዋሚ። 3. እርስ በርስ የማይስማማ። 4. ለአንዱ ቃል ፍቺ ተፃራሪ ፍቺ ያለው ቃል። *"መጣ" "ሄደ" ተቃራኒ ነው።*

ተቃራኒ ፆታ ስ በፆታ የማይመሳሰል (እንስትና ተባእት)። የተባእት ተቃራኒ ፆታ እንስት ስትሆን የእንስቷም ተቃራኒ ፆታ ተባእት ነው።

ቀረነተ (ቀረነጠ) ግ ጠረነቀ፥ ጥፍር አድርጎ አሰረ።

ቀረና ግ 1. ቀንድ፥ ቆዳ፥ ፀጉር፥...ሲቃጠል እንደሚፈጠረው ያለ ሽታ ሸተተ። 2. ገማ፡ ከረፋ። 3. ጎረና (ለወጥና ለመሳሰለው)።

ቅርናት ስ 1. ከተቃጠለ ቀንድ ወይም ቆዳ ወይም ፀጉር የሚወጣ መጥፎ ሽታ። 2. ክርፋት፥ ግማት።

ቅርናታም ቅ (ስድብ) ግማታም፡ ክርፋታም።

አቀረና ግ መታ (በዱላ፥ በጥፊ፥...)።

ቀረንጠሎ ስ የተበጣጠሰና ያደፈ ልብስ፡ ቁርንቀስ፥ ቅርንጥስ።

ቀረንጠሏም ቅ (ስድብ) የተበጣጠሰና ያደፈ ልብስ የሚለብስ፡ ቅርንጥሳም፥ ቡትቷም።

ቀረዋ^1 "ቀራዎ^1" ን ተመ.

ቀረዋ^2 "ቀራዎ^2" ን ተመ.

ቀረደደ ግ 1. ቀረጠ፥ ሸረከተ። 2. ቀረጠፈ፥

ሰነጠቀ። 3. (ዘይ.) ሳያፍር ዋሸ፤ ወሸከተ።

ተቀረደደ ግ 1. ተቀደደ፣ ተቆረጠ፣ ተሸረከተ፣ ተሰነጠቀ። 2. (ዘይ.) ሳያፍር ዋሸ፤ ወሸከተ።

ተቀራደደ ግ በስለት ተሸራከተ።

***ቀረደደ**

ቀረደድ(ቀርዳዳ) ቅ ከረፈፍ፣ ቀረፈፍ፤ ከርፋፋ፣ ቀርፋፋ።

ተንቀረደደ ግ ተንከረፈፈ፣ ተንቀረፈፈ (ለአካሄድ)።

አንቀረደደ ግ አንከረፈፈ፤ አንቀረፈፈ።

ቀረጠ ግ ግብር ተቀበለ ወይም አስከፈለ (ከሸያጭ ወይም ከሌላ ገቢ፤ ጥቅም)።

ቀረጥ ስ 1. ከሸያጭና ግዢ ወይም ከሌላ ነገር ለተገኘ ገቢ ወይም ጥቅም ለመንግስት የሚከፈል ግብር፣ ታክስ፣ አሹራ። 2. በፊደል ተራው ተመ.

የቀረጥ ቴምብር ስ ለመንግስት ገቢ እንዲያስገኝ ባለጉዳይ እየገዛ በማመልከቻ፣ በልዩ ልዩ የፈቃድና የምስክር ወረቀት፣ የንግድ እቃ፣... ላይ የሚለጠፍ ቴምብር።

ቀራጭ ስ በገቢያ መግቢያ በሮች፣ በመንገድ ኬላዎች ላይ እየተገኘ ቀረጥ የሚያስከፍል የመንግስት ሰራተኛ።

ቅርጫ ስ ክፍፍል፣ ቅርምት (የስጋ)።

ተቃረጠ ግ ተከፋፈለ፤ ተቀራመተ (ስጋን)።

አቃረጠ ግ አከፋፈለ፤ አቀራመተ (ስጋን)።

ቀረጠፈ ግ 1. ከጫፍ ከጫፉ ላይ በአጭሩ በአጭሩ ቆረጠ፤ ከረተፈ (ጌሾን ወይንም ሌላ ነገርን)። 2. ጎመደ፣ ቆረጠ። 3. አጣበቀ፤ ቆነጠጠ፤ ቆረጠ። *መዝጊያው እጄን ቀረጠፈኝ*። 4. በላ፤ አነከተ። *ጅብ ቀረጠፈው*። 5. አመመ (ቁርጥማት)።

መቀርጠፊያ ስ አነስተኛ መጥረቢያ።

ቀረጥ^{1} ስ ቅጠሉ ለቁርበት ማቅለሚያ፣ ላልተሟሸ ወይም ለአዲስ ቅል ማሟሻ የሚሆን አነስተኛ የዛፍ አይነት።

ቀረጥ^{2} "**ቀረጠ**" ስር ተመ.

***ቀረጨ**

አንቀራጨ ግ ቅርጭው ቅርጭው አደረገ፣ ቆረጠመ።

ቀረጨመ "**ቆረጨመ**" ን ተመ።

ቀረጨጨ ግ በሃይል ነከሰ (በጥርስ)።

ቀረፀ (ቀረጸ) ግ 1. አነፀ፤ አበጀ፤ ቅርፅ ሰራ። 2. አሾለ። *እርሳሱን ቀረፀ*። 3. ቀዳ፣ መዘገበ፤ አነሳ (ድምፅን፣ ምስልን፣... በቴፕ፣ በፊልም፣...)። 4. ፈጠረ፤ ሳለ (አንድን ስሜት በአእምሮ ውስጥ)። 5. ሰራ፤ አበጀ (ለምሳሌ ፊደልን)።

መቅረጫ ስ በውስጡ ስለት ያለው የእርሳስ ማሾያ።

ቀራጭ (ቀራፂ) ስ ሃውልት፤ ምስል ሰሪ።

ቅርፅ ስ 1. ከእንጨት ወይም ከድንጋይ ወይም ከነሃስ፣...የተሰራ የአንድ ነገር ምስል። 2. የአንድ ነገር ውጫዊ ገፅታ፣ መልክ። 3. የሰውነት አቋም፣ ቁመና።

ቅርፃ ቅርፅ ስ ከእንጨት ወይም ከድንጋይ ወይም ከነሃስ፤...የተሰሩ የልዩ ልዩ ምስሎች፣ እቃዎች፤... አሰራርና አይነት።

ቀረፈ ግ 1. አነሳ፣ ሳበ፣ ገለፈፈ (ቅርፊትን፤ ምርጊትን፤...)። 2. ተወ፤ አስወገደ (ቂምን፤ ችግርን)።

ቀራፋ ቅ የሙጋድ እንጨት ሰባሪ፣ ፈላጭ፤ አቅራቢ።

ቀራፎ ስ 1. የቅል፣ የአንኮላ ጉማጅ፣ ፋጋ። 2. (ዘይ፤ ስድብ) ከርፋፋ፤ ቂል።

ቅራፊ ቅ ተቀርፎ፣ ተገልፍፎ ከላይ የተነሳው የእንጨት ወይም የሌላ ነገር ቅርፊት።

ቅርፊት ስ ከላይ ተቀርፎ፣ ተልጦ የተነሳ የእንጨት፣ የዳቦ፣... ልባስ፣ ሽፋን።

ቅርፊት ያዘ/አበጀ ቅርፊት ለበሰ፤ ደረቀ (ቁስል)።

ቅርፍርፍ ቅ ስንጥቅጥቅ፣ ፍርክርክ።

ተቀረፈ ግ ተነሳ፤ ተሳበ፣ ተገለፈፈ።

ተቅረፈረፈ ግ ተሰነጣጠቀ፤ ተፍረከረከ።

ቀረፈተ ግ ቀረፈ፣ ሳበ፣ ገሸለጠ።

ተቀረፈተ ግ ተቀረፈ፤ ተሳበ፣ ተገሸለጠ።

ቀረፈፈ ግ ሳበ፤ መለጠ፤ ገፈፈ፤ ገለፈፈ፤ ቀረፈ።

***ቀረፈፈ**

ቀረፈፍ(ቀርፋፋ) ቅ ከረፈፍ፤ ከርፋፋ።

ተንቀረፈፈ ግ 1. ዝግ አለ፤ ተንከረፈፈ፤ ፍጥነት አጣ። 2. ረዘመ፤ ተንቀረበበ።

ተንቀራፈፈ ዝ.ከ.

አንቀረፈፈ ግ አንከረፈፈ፣ አረዘመ፣ አንቀረበበ።

አንቀራፈፈ ዝ.ከ.

ቀረፋ ስ በቅመምነት የሚያገለግል ጥሩ ጣእምና ሽታ ያለው የእንጨት ቅርፊት።

ቀሪቦ ስ ጌሾ የሌለውና በጠላ መልክ የሚዘጋጅ መጠጥ።

ቀራ^{1} ግ ከብቶችን ሊሊት ጠበቀ።

ቅራት ስ የሌሊት ከብት ጥበቃ። *ቅራት ወጣ*።

ቀራተኛ ስ ሌሊት ከብት የሚጠብቅ ሰው።

ቀራ^2 ግ ቁርአን ተማረ።

ቀራሮ "**ቀረሮ**" ን ተመ.

ቀራዎ^1 (**ቀረዋ**) ስ መስፈሪያ ቁና። (ሃረር)

ቀራዎ^2 (**ቀረዋ**) ስ የጎራዴ አይነት።

ቀራጭ^1 "**ቀረጠ**" ስር ተመ.

ቀራጭ^2 "**ቀረፀ**" ስር ተመ.

ቀራጺ "**ቀረጠ**" ስር "**ቀራጭ**" ን ተመ.

ቀራፊ "**ቀረፈ**" ስር ተመ.

ቀራፎ "**ቀረፈ**" ስር ተመ.

ቀርም "**ቃረመ**" ስር "**ቃርሚያ**" ን ተመ.

ቀርቀም ስ ፈጦ የሚመስልና ፍሬው የማይበላ ወንዝ ዳር የሚበቅል የእፀዋት አይነት።

ቀርቀሬ "**ቀረቀረ**" ስር ተመ.

ቀርቀር ዝ.ከ.

ቀርቀቦ "**ቀርበቦ**" ን ተመ.

ቀርቃሃ "**ቀርከሃ**" ን ተመ.

ቀርቃባ "**ቀረቀበ**" ስር ተመ.

ቀርበቦ (**ቀረቦ፣ ቀርቀቦ**) ስ ከላም ወይም ከበሬ ግምባር ቆዳ የሚሰራ ወታቦ መሰል ቅርጫት ወይም ቁና መሰል ትንሽ እቃ።

ቀርበታ ስ 1. ለውሃ መቅጃ የሚያገለግል ስልቻ። 2. (ዘይ.፣ ስድብ) ሆዳም፤ ቀፈታም።

ቀርባባ "***ቀረበበ**" ስር ተመ.

ቀርን ስ ቀንድ።

ቀርከሃ (**ቀርቃሃ**) ስ አንድ ቦታ እጅብ ብሎ የሚበቅል እንደሸንበቆ ያለ ግን ትልልቅና ጠንካራ የሆነ የእፀዋት አይነት።

ቀርዳዳ "***ቀረደደ**" ስር "**ቀረደድ**"ን ተመ.

ቀርጥ ስ ስፋቱ ሃምሳ ሜትር በሃምሳ ሜትር ወይም 50 መረብ የሆነ መሬት።

ቀርጫ

ቀርጫ ቀርጫ አለ ግ ሲበሉት ቀጭ ቀጭ የሚል ድምፅ ሰጠ።

ቀርፋፋ "***ቀረፈፈ**" ስር "**ቀረፈፍ**"ን ተመ.

ቀሰመ ግ 1. ጣፋጭ ፈሳሽን ከአበባ ውስጥ ወሰደ፤ ሰበሰበ፣ ለቀመ (ንብ፣ቢራቢሮ)። 2. ተማረ፤ ወሰደ። *ጎበዝ ተማሪ እውቀትን ከመምህሩ ይቀስማል።*

ቀሰም ስ ከቀጭን መቃ ወይም ሸንበቆ ባጭር ባጭሩ ተቆርጦ የተዘጋጀ የማግ ማጸወሪያ፣ መጠቅለያ።

ቀሰረ ግ 1. አቆመ፤ ገተረ (ጭራን፣ ጣትን፣...)።

ቀሳራ (**ቅስር**) ቅ ገታራ፣ የተቀሰረ።

ቅስር ቅስር አለ ግ ግትር ግትር አለ (ለአካሄድ)።

ተቀሰረ ግ ተገተረ፣ ቆመ።

ቀሰሰ^1 ግ የቅስናን ማእርግ ወይም ስልጣነ ክህነትን ተቀበለ፤ ቄስ ሆነ።

ቀሲስ ስ ስልጣነ ክህነት ያለው የቤተክርስቲያን አገልጋይ፣ ካህን።

ቄስ (ብ.ቁ. **ቀሳውስት**) ዝ.ከ.

ቄሰ ገበዝ "**ገበዝ**" ን ተመ.

ቄስአጤ ስ በቀድሞ ዘመን የንጉስ ነፍስ አባት፤ ዘውድ አጣኝ፣ ማእድ ባራኪ የነበረ ካህን።

የቄስ በቅሎ እየሄደ ሳለ መንገድ ላይ ሰው ባገኘ ቁጥር በየቦታው የሚቆም፤ የሚገተር።

የቄስ ተማሪ ስ 1. ከፊደል ቆጠራ እስከ ዳዊት ድገማ ያለውን ትምህርት በቄስ ትምህርት ቤት የሚከታተል ተማሪ። 2. የቆሎ ተማሪ።

የቄስ ትምህርት ቤት ስ ህፃናት በመጀመሪያ ከፊደል ቆጠራ እስከ ዳዊት ድገማ የሚማሩበት በየመንደሩና በየቤተክርስቲያኑ የሚገኝ ትምህርት ቤት።

ቅስና ስ የቄስነት ማእርግ፣ ስልጣን።

አቀሰሰ ግ ቅስና ሰጠ፤ ቄስ አደረገ።

ቀሰሰ^2 ግ ፈዘዘ፣ ቀዘዘ።

ቀሰስተኛ ቅ በበሽታ፣ በተፈጥሮ፣...ምክንያት አቅም ያጣ፣ ዝግ ብሎ የሚራመድ። 2. ፈዛዛ።

ቀሳሳ ቅ ቀዛዛ፣ ፈዛዛ።

ቅስስ አለ ግ ፍዝዝ፣ ቅዝዝ አለ።

ቀሰቀሰ ግ 1. አበነነ፤ አነቃ (ከእንቅልፍ)። 2. አስተማረ፣ አነቃ፣ አነሳሳ (አንድ ነገር ለመስራት)። 3. እንደገና እንዲነሳ፣ እንዲታወስ አደረገ። *ትዝታውን ቀሰቀሰበት።* 4. ጀመረ፣ አጫረ። *ጠቡን የቀሰቀሰው ልጅየው ነው።* 5. በረበረ፣ ፈተሸ፣ ፈለገ (እቃን)። 6. ነካካ፤ አወከ (ቢታውን እንዲለቅ)። *ንቡን ከቀፎው ቀሰቀሰው።* 7. አጫረ፣ አነሳሳ። *የወጡ ሽታ የምግብ ፍላጎቷን ቀሰቀሰባት።*

ቅስቀሳ ስ ሰዎችን ለአንድ አላማ ወይም ስራ ለማሰለፍ የሚሰጥ ማነቃቂያ፣ ማነሳሻ፣ መጎትጎቻ ትምህርት።

ቀስቀስ አለ ግ በጥቂቱ ተንቀሳቀሰ፣ ተላወሰ።

ቅስቅስ አለ ግ ንቅንቅ አለ። *ቅስቅስ አንገቶታል።*

ቅስቅስ ብሎ ወጣ በጠቅላላ፣ በብዛት ወጣ።

ተቀሰቀሰ ግ እንደገና ተነሳ፤ ተጀመረ።

ተቀስቅሶ ወጣ በብዛት ወጣ።

***ቀሰቀሰ**

ቅስቃሴ ስ ንቅናቄ፣ እንቅስቃሴ።

ተንቀሳቀሰ ግ 1. ተነቃነቀ፤ ተሳወሰ። 2 ጉዞ ጀመረ፥ ተነሳ። 3. ወዲያ ወዲህ አለ፥ ተዘዋወረ (ከቦታ ወደ ቦታ)።

መንቀሳቀሻ ስ መነሻ፤ መጀመሪያ የሚሆን ገንዘብ (ለንግድ ስራ)።

ተንቀሳቃሽ ቅ 1. ከቦታ ወደ ቦታ ሊዘዋወር የሚችል። 2. የሚሳወስ፤ ህይወት ያለው ነገር።

ተንቀሳቃሽ ሂሳብ ስ ወለድ የማይኖረውና በተፈለገ ጊዜ በቼክ ሊወጣ የሚችል በባንክ የሚቀመጥ ገንዘብ።

አንቀሳቀሰ ግ 1. አነቃነቀ፥ አሳወሰ። 2. አስጀመረ፥ አስነሳ (ሞተርን፥...)። 3. አካሄደ፥ መራ። *ድርጅቱን የሚያንቀሳቅሰው ማነው?* 4. ገንዘብን ወጪ ገቢ አደረገ፥ በስራ ላይ አዋለ።

እንቅስቃሴ ስ 1. የመነቃነቅ፥ የመሳወስ ሁኔታ። 2. አንድን ስራ ለመስራት የሚደረግ መሯሯጥ። 3. የተቃውሞ ርምጃ፤ ንቅናቄ፥ አመፅ።

ቀሰብ ስ ማንኛውም እንደ መቃ ያለ ውስጠ ክፍት እንጨት ወይም ብረት።

ቀሰተ ግ 1. ቅስት ሰራ፥ አበጀ፤ አጎበበ፤ እንደ ደጋን አደረገ።

ቀስት ስ 1. በደጋን አይነት ወይም ቅርፅ የተሰራና ገመዱን ለጥጠው ሲለቁት ፍላፃ የሚያስፈነጥር የጦር መሳሪያ። 2. ጫፉ ሹል የሆነና በደጋን አውታር የሚስፈነጠር፥ለጦር መሳሪያነት የሚያገለግል ብረት፤ ፍላፃ። 3. በፍላፃ ምስል የተሰራ የአቅጣጫ ማመልከቻ ምልክት።

ቀስተደመና ስ የተለያዩ ቀለማት (አረንጓዴ፥ ቢጫ፥ ቀይ፥...) ያለውና በተለይ ካፊያ በሚኖርበት ጊዜ በደጋን ቅርፅ ከሰማይ ወደመሬት ተተክሎ የሚታይ የፀሃይ እንፅብራቂ፤ የማርያም መቀነትም ይባላል።

ቀስተኛ ስ በቀስት የሚዋጋ፥ የሚያድን ሰው።

ቅስት ስ 1. በበር፥ በመተላለፊያ፥ በድልድይ ላይ እንደ ደጋን ጎብጦ ወይም በአራት ማእዘን ቅርፅ ሆኖ የሚሰራ እንጨት፤ ብረት ወይም ግምብ። 2. እንደ ጠረጴዛ እግር ወይም የማድግጸ ቋሚ እንጨት የመሳሰለ ነገር እንዳይዋልልና እንዳይወድቅ ወጥሮ የሚይዝ ሰያፍ ማገር።

ቀሰንዲ ቅ ቆሸማዳ፥ ወልጋዳ።

ቀሰጠ ግ 1. ቆንጠር አድርጎ ሰረቀ፤ ቀንሶ ወሰደ። 2. አበላ፥ ቀጠፈ፥ ዋሸ።

ቀሳጢ ቅ 1. ሌባ። 2. አባይ፥ ዋሾ።

ቀሰፈ ግ 1. ያለጊዜው ገደለ፥ ቀጠፈ፥ ቀጨ። 2. ሰቀዘ፥ ወጠረ፤ አስጨነቀ (ውጋትና የመሳሰለው)።

ቀሰፎ ያዘ ወጥሮ፥ አስጨንቆ፤ ወግቶ ያዘ።

መቅሰፍት ስ እልቂትን የሚያስከትል እንደተላላፊ በሽታ፥ ጎርፍ፥ የመሬት መንቀጥቀጥ፤ ቸነፈር የመሳሰለ ከባድ አደጋ፤ መአት።

መቅሰፍታም ቅ መቅሰፍት፤ በሽታ የሚበዛበት (ቦታ፤ ጊዜ)።

ቀሳፊ ቅ ገዳይ፥ አጥፊ። *የቀሳፊው ኤድስ ስለባ ላለመሆን ከልቅ ወሲብ መቆጠብ ያስፈልጋል።*

ቅሰፈት ስ 1. በአጭር መቀጨት፤ በድንገት መሞት። 2. ሞት የሚያስከትል አደጋ፤ መአት፥ በሽታ፤...።

ተቀሰፈ ግ ያለጊዜው ሞተ፥ ተቀጨ፤ ተቀጠፈ። 2. ፉታ አጣ፤ ተወጥሮ ተያዘ። *ታቀሰፎ ተይዟል።*

ቀሲስ "**ቀሰሰ^{1}**" ስር ተመ.

ቀሳ ስ ተላላፊ በሽታ ወደ ጤነኛው ሰው እንዳይተላለፍ ከሰፈር ራቅ ብሎ በሚገኝ ገለልተኛ ቦታ ላይ ለበሽተኛው መታመሚያ የሚሰራ ጊዜያዊ ቤት።

ቀሳ ወጣ ገለል ወዳለ ቦታና ቤት ውስጥ እንዲቀመጥ ተደረገ (በሽታ የያዘው ሰው)።

ቀሳራ "**ቀሰረ**" ስር ተመ.

ቀሳሳ "**ቀሰሰ^{2}**" ስር ተመ.

ቀሳውስት "**ቀሰሰ^{1}**" ስር ተመ.

ቀሳጢ "**ቀሰጠ**" ስር ተመ.

ቀሳፈተ ግ ቀላመደ፥ ዘላበደ፤ አበለ፤ ዋሸ።

ቀሳፋች ቅ (ስድብ) ቀባጣሪ፥ ለፍላፊ፤ ውሸት የሚያበዛ።

ቀስፋታ ዝ.ከ.

አስቀሳፈተ ግ አስዋሸ፥ አሳበለ፥ አስቀባዠረ።

ቀሳፊ "**ቀሰፈ**" ስር ተመ.

ቀሳፋች "**ቀሳፈተ**" ስር ተመ.

ቀስ ዝግ፥ ረጋ።

ቀስ በቀስ ተው.ግ. በጊዜ ብዛት፤ በዝግታ፥ ቀስ እያለ። *ቀስ በቀስ እንቁላል በእግሩ ይሄዳል።*

ቀስታ ስ ዝግታ፥ ርጋታ።

በቀስታ ተው.ግ. 1. በዝግታ፥ በርጋታ። 2.በዝቅተኛ ድምፅ ፥ በሹክሹክታ፥ በለሆሳስ። *የተኛትን እንዳትቀሰቅሱ በቀስታ ተነጋገሩ።*

ቀስተኛ ቅ ዝግተኛ፥ ዘገምተኛ።

ቀስ አለ ግ 1. ዝግ አለ፤ ረጋ አለ፥ ከመጣደፍ ተቆጠበ። *ቀስ እያለ ተራመደ።* 2. ከፍ ያለ ድምፅ ሳያሰማ ወይም ሙከ ሳይል ወይም ሃይል ሳያበዛ፥... አደረገ። *ቀስ ብለው ይናገሩ እባክዎ* /ምስማሩን በመዶሻ ቀስ እያለ ቀጥቅጦ አቃናው።

ቀስ አደረገ ግ 1.ፍጥነት ቀነሰ፥ ዝግ አደረገ። 2. በዝግታ፥ በእርጋታ፥ በጥንቃቄ፥... አደረገ። *በሽተኛውን ከአልጋው ላይ ቀስ አድርጎ*

ለሰተኛው። 3. በትንሹ፥ ሃይል ሳይጨምር ስራ ወይም አደረገ። *ጻሩን ቀስ አድርገህ ምታ*።

ቀስተኒ(ን)ቻ ስ መጠኑ ከዕጌረዳ የማይበልጥ፥ ግንዱ ውስጡ ክፍት፥ የሚለመጥ፥ ለቀስት የሚሆን የእፀዋት አይነት፥ ሰሬቴ።

ቀስተኛ "ቀሰተ" ስር ተመ.

ቀሰተደመና "ቀሰተ" ስር ተመ.

ቀሲታ "ቀሰ" ስር ተመ.

ቀስት "ቀሰተ" ስር ተመ.

ቀስፉታ "ቀሳፈተ" ስር ተመ.

ቀሸመ ግ (የእራዳ አነ.) አንድን ነገር የመስራት፥ የማድረግ ዘዴው፥ እውቀቱ፥ ችሎታው፥ ብልሃቱ ቀነሰ።

ቀሽም ቅ 1. አንድን ነገር በሚገባ መስራት ወይም ማድረግ የማይችል፤ ዘቂ ሙያ የሌለው። *እገሩ ኳስ ሲጫወት ቀሽም ነው*። 2. ከሽ፥ የማይረባ፥ ጥራት የሌለው። *ያደረገችው ጫማ ቀሽም ነው*።

ቀሸመደ ግ 1. ሰበረ፥ እነከተ። 2. መታ፥ አዘረጠ (በብትር)።

ቀሽማዳ (ቀሸመድ) ቅ ሰባራ፥ ደካማ፥ አቅመቢስ፥ ተልካሻ።

ቅሽምድምድ ቅ ውልክፍክፍ፥ ልፍስፍስ፥ አቅመቢስ።

ቀሸረ ግ 1. ከሸነ፥ አሳመረ። 2. በመውቀጥ ወይም በመከካት ፍሬውን ከገለባ ለየ (ብዙውን ጊዜ ለቡና)።

ቀሸር(ቅሸር) ስ ገለባው ወይም ቆዳው ከላዩ ላይ የተነሳለት ቡና፥ የተፈለፈለ ቡና።

ተቀሸረ ግ ተከሸነ፥ አማረ።

ቀሸረረ ግ ከሳ፥ ደረቀ።

ቀሽራራ (ቀሸረር) ቅ ከሲታ፥ ደረቅ።

ተንቀሸረረ ግ ከሳ፥ ደረቀ።

አንቀሸረረ ግ አከሳ፥ አደረቀ (ሰውነትን)።

***ቀሸቀሸ**

ተንቀሸቀሸ ግ ተነካከተ፥ ተሰባበረ።

አንቀሻቀሸ ግ ሰባበረ፥ አነካከተ።

እንቅሽቅሽ አለ ግ እንክትክት፥ ስብርብር አለ።

እንቅሽቅሽ አደረገ ግ እንካከተ፥ ሰባበረ።

ቀሸመሪ (ሬ) ስ የቀድሞ ጊዜ ጌጠኛ ቀብጣብ፥ መታጠቂያ።

ቀሽማዳ "ቀሸመደ" ስር ተመ.

ቀሽም "ቀሸመ" ስር ተመ.

ቀሽራራ "ቀሸረረ" ስር ተመ.

ቀሸር^{1} "ቀሸረ" ስር ተመ.

ቀሸር^{2} ስ ያለሻይ ቅጠል በዝንጅብል ብቻ የተፈላ ሻይ።

ቀቀለ ግ 1. በውሃ ውስጥ አድርጎ በሙቀት ሃይል አበሰለ፥ አምከከ፥ አነፈረ (ብዙውን ጊዜ ለምግብ)። 2. አቃጠለ፥ ለበለበ፥ (በረሃው፥ ሙቀቱ፥...)።

መቀቀያ ስ የሚቀቀልበት፥ እንደድስት፥ ማሰሮ፥ ብረት ድስት፥ ሰታቴ ያለ እቃ።

ቀቃይ ስ አብሳይ።

ቅቅል ስ 1.ተቀቅሎ የበሰለ ስጋ ከነመረቁ። 2.የተቀቀለ (በቆሎ፥...)።

ተቀቀለ ግ 1. በሰለ፥ ሞከከ፥ ነፈረ (በውሃና በሙቀት)። 2. ተቃጠለ፥ ተለበለበ (በፀሃይ፥ በበረሃ ሙቀት፥...)።

ቀቀሬ ግ ጆሮውን ጣለ፥ ለማዳመጥ፥ ለመስማት ጆሮውን አቆመ። *ጆሮውን ቀቅሮ ያዳምጥ ነበር*።

ቀቀተ ግ ነፈገ፥ ሰሰተ።

ቅቅት (ቀቀት) ስ ንፍገት፥ ስስት።

ቅቅታም ቅ (ስድብ) ንፉግ፥ ስስታም።

ቀቃይ "ቀቀለ" ስር ተመ.

ቀቅ^{1} ስ በማላ ላይ ያለ እሀልን የሚያበላሽ ወሮጭ፥ ሞግ።

ቀቅ^{2} ስ ለተመታና ለቆሰለ ሰው የሚሰጥ እነስተኛ ካሳ። *እገሌ የቀቅ ከፈለ*።

***ቀበለ**

ቀበሌ ስ የሰውን ድምፅ ተቀብሎ የሚያስተጋባ የገደል ማሚቶ።

ቅበላ ስ የፆም ዋዜማ፥ ፆም ከመግባቱ በፊት ቀደም ብሎ ያለው ቀን ወይም ሰሞን።

ቅብብል ስ አንዱ ለሌላው የሚያደርገው የመስጠት፥ የማቀበል፥ የማሻገር ድርጊት። *እቃው የተጓጓዘው በቅብብል ነው*።

ቅብብሎሽ ዝ.ከ.

ተቀበለ ግ 1. ወሰደ፥ እጁ አደረገ፥ ተረከበ። 2.ተስማማ፥ ፈቀደ፥ እሺ አለ። *የቀረበውን ሃሳብ ኮሚቴው ተቀበለው*። 3. አመነ፥ የራሱ አደረገ። *ክርስትናን ተቀበለ*። 4. የመጣን እንግዳ አስተናገደ። 5. ተስማሚ ሆነ፥ አማረ። *የለበሰው ልብስ ተቀብሎታል*። 6.አየ፥ ደረሰበት፥ ተሸከመ። *መከራ ተቀበለ/ስቃይ ተቀበለ*። 7. አገኘ፥ ወሰደ(ስልጣንን፥ማእረግን፥ ሃላፊነትን፥...)። *ሺቃና ተቀበለ*። 8. (በዘፈን፥ በሙሾ፥... ጊዜ አውራጁን በድምፅ አጀበ፥ አደመቀ፥ አዝማቹን አለ፥ አዜመ።

ተቀባበለ ግ 1. አንዱ ለሌላው እየሰጠ አስተላለፈ፥ አሸጋገረ። 2. ጠመንጃው ወይም ሽጉጡ ጥይት ጎርሶ ለተኩስ ተዘጋጀ፥ ከቃታው ወደ ጋን ገባ።

አቀበለ ግ ሰጠ፥ አሻገረ፥ አሳለፈ::

አቀባበለ ግ ጠመንጃውን አጉርሶ ለተኩስ አዘጋጀ፤ ጥይቱን ወደ ጎኑ አስገባ::

ማቀባበያ ስ የጎረሰን ጥይት ለተኩስ ማዘጋጃ፤ ወደ ጎኑ ማስገቢያ::

አቀባበል ስ 1. እንግዳን የመቀበልና የማስተናገድ ስነ ስርአት:: *ዛሬ ከውጭ የመጡት እንግዳ ከፍ ያለ አቀባበል ተደረገላቸው::* 2. መስተንግዶ:: *ሴትየዋ እንግዳ አቀባበል ያውቃሉ::*

ቀበሌ ስ 1. ሰፈር፥ መንደር፥ አጥቢያ:: 2. ነዋሪዎች በማህበር ተደራጅተው የሚተዳደሩበት የተወሰነ ክልል የያዘ ቦታ፥ አካባቢ:: 3. ያንድ ከፍተኛ ከተማ ንኡስ ክፍል:: 4. የከተማ ነዋሪዎች ማህበር ፅህፈት ቤት::

ቀበሌ ገበሬ ማህበር ስ በተወሰነ ክልል(ብዙውን ጊዜ በየሃያ ጋሻ) ክልል ውስጥ የሚገኙ ገበሬዎች በማህበር ተደራጅተው የሚገኙበትና የአስተዳደር፥ የኢኮኖሚ፥ የሶሻልና የፖለቲካ ጉዳዮችን በአጠቃላይ የመከታተልና የማስተባበር ተግባር የሚያከናውን ማህበራዊ ድርጅት:: ገበሬ ማህበር እየተባለም ይጠራል::

ቀበሌ “*ቀበለ” ስር ተመ.

ቀበረ ግ 1. ሬሳን ወይም ሌላን ነገር ጉድጓድ ውስጥ አስገብቶ በአፈር፥ በድንጋይ፥... ጉድጓዱን ሞላ፤ ደፈነ:: 2. በቀብር ስነ ስርአት ላይ ተገኘ:: 3. ደበቀ፥ ሰወረ፥ ሸሸገ:: 4.(ዘይ.) ጨቆነ፥ እድገት ከለከለ (የደመወዝ፥ የስልጣን፥...):: 5. ኳስን ወደተጋጣሚው ወገን በኩል አክርሮ ቁልቁል መታ (የመረብን፥ የጠረጴዛ ቴኒስን ኳስ፥...)::

መቃብር ስ የሬሳ ማኖሪያ ጉድጓድ፤ ቦታ::

መቃብር ቆፋሪ ስ የመቃብር ቦታን እየቆፈረ የሚያዘጋጅ (ሰው)::

መቃብር ቤት ስ ብዙውን ጊዜ መነኩሳት፥ የቆሎ ተማሪዎች፥...የሚኖሩበትና በቤተክርስቲያን ክልል ውስጥ የሚገኝ፥ በሙታን መቃብር ላይ የተሰራ ቤት::

ቀባሪ ስ 1. ወደ መቃብር ቦታ ሬሳን አጅቦ የሚሄድ ለቀስተኛ:: 2. ጉድጓድ ቆፍሮ ሬሳውን አፈር የሚያለብስ::

ቀባሪ አታሳጣኝ የክፉ ቀን ወገን፥ ዘመድ አታሳጣኝ ለማለት የሚነገር አባባል::

ለቀባሪው አረዱት ጉዳዩን በይበልጥ ለሚያውቀው ሰው እንደማያውቅ አድርገው ነገሩት::

ቀብር ስ 1. ሬሳን ለመቅበር የሚደረግ ስነስርአት፤ ስርአተ ቀብርም ይባላል:: 2. አስከሬን የሚቀበርበት ቦታ፥ ጉድጓድ፤ መቃብር::

ተቀበረ ግ 1. ወደ መቃብር ገባ፤ አፈር ለበሰ:: 2. ተደበቀ፥ ተሸሸገ፥ ተሰወረ:: 3.እድገት አጣ፥ ተከለከለ (የደመወዙ፥ የስልጣን፥...)::

አያቀባብርም ያቀያይማል፤ ያጣላል፥ ያጨቃጭቃል (ነገሩ፥ ጉዳዩ፥ ድርጊቱ)::

አቀበረ ግ የዳን መስሎ መግል ያዘ፤ ለገመ (ቁስል)::

አቃበረ (አቀባበረ) ግ 1. ሬሳን ለቀብር አጅቦ ወሰደ:: 2. በቀብሩ ስነስርአት ላይ ተገኘ፥ አገዘ፥ ረዳ::

አስቀበረ ግ በቀብሩ ስነስርአት ላይ ተገኘ::

***ቀበረረ**

ቀብራራ (ቀበረር) ቅ 1. ደልቃቃ:: 2. ሞልቃቃ፥ ልቅ ሆኖ ያደገ::

ቅብርር አለ ግ ተንቀባረረ::

ቅብርር አደረገ ግ አንቀባረረ::

ተንቀባረረ ግ 1. ተቀማጠለ፤ ተንደላቀቀ:: 2.ተሞላቀቀ፤ ተኩራራ::

አንቀባረረ ግ 1. አቀማጠለ፥ አንደላቀቀ:: 2. አሞላቀቀ፥ አኩራራ::

ቀበርቾ ስ ብዙውን ጊዜ በደጋ የሚበቅል፥ እሾህ ያለውና ስሩ ለመድሃኒትነት የሚያገለግል የእፅዋት አይነት::

ቀበሮ ስ በብዛት ቀይ ዛጎልማና ወርቅማ መልክ፤ ሾጣጣ ጆሮዎችና ረጅም እግር ያለው፥ ጅራቱ ረጅምና በጣም ፀጉራም የሆነ፤ ትናንሽ የቤት እንስሳትንና እንቁላል የሚመገብ ስጋ በል የዱር እንስሳ(ስእሉን የዱር እንስሳ ስር. ተመ.)::

የቀበሮ ባህታዊ ቅ አስመሳይ፥ አታላይ፥ አሳሳች፤ የዋህ፥ ደግ መስሎ በመጠጋት የሚያጠፋ፥ የሚጎዳ::

የቀበሮ ጉድጓድ ስ በጦርነት ጊዜ ወታደሮች ለመከላከያ ወይም ለመሸሸጊያ የሚጠቀሙበት ጉድጓድ፥ ጉድባ፥ ምሽግ::

ቀበቀበ^{1} ግ መሬትን ደጋግሞ አረሰ፥ አለሰለሰ::

ቅብቅብ ስ ተደጋግሞ የታረሰ፥ ልስልስ እርሻ::

ቀበቀበ^{2} ግ 1. የደነዘን ብረት አሾለ፥ አሰላ፥ አተባ:: 2. ቸከለ፥ ተከለ፥ ወጋ፥ ወደ ውስጥ አስገባ (ችካልን):: 3.መታ፥ ቆረቆረ፥ አንኳኳ (በርን)::

ቅብቃብ ስ ችካል::

***ቀበቀበ**

ቀብቃባ(ቀበቀብ) ቅ ገብጋባ፥ ስስታም፥ ቅቅታም፤ መስጠት ወይም ማውጣት የማይፈልግ፥ ቆንቋና::

ቅብቅብ አለ ግ ተንቀበቀበ::

ተንቀበቀበ ግ ተንገበገበ፥ ሰሰተ፥ ቀቀተ::

አንቀበቀበ ስ አንገበገበ፤ አሰሰተ፥ አቀቀተ::

ቀበተተ ግ ነፋ፥ ወጠረ። *ከበላሁት ምግብ ሆዴን ቀበተተኝ።*

ቀብታታ (ቀበተት) ቅ የተነፋ፥ የተወጠረ፥ ያበጠ (ሆድ፥ ስልቻ...)።

ቅብትት ዝ.ከ.

ተቀበተተ ግ ተነፋ፥ ተወጠረ።

ቀበቶ ስ 1. ከቆዳ ወይም ከሸራ ወይም ከወርቅ፣... የሚሰራና ወገብ ላይ የሚውል መታጠቂያ፣ ሰቅ። 2. በበረራ፥ በጉዞ ላይ ከአደጋ ለመከላከል እንዲረዳ በመኪና ወይም በአውሮፕላን ወንበር ላይ ሆኖ ተሳፋሪው ወይም ነጂው የሚታጠቀው ቀበቶ መሰል ሸራ፥ ቆዳ።



ቀበቶ ና ቀፎ

ቀበቶህን አጥብቅ በርታ፥ ጥና፥ ጠንክር።

ቀበኛ ስ 1. ልብስና የመሳሰለውን የሚበላ ከብት። 2. (ዘይ.) (ልብስ ፥ እህል) ቶሎ የሚጨርስ፣ የማይበረክትለት።

ቀበዝባዛ "ቃበዘ" ስር ተመ.

ቀበደደ ግ 1. ነፋ፥ ወጠረ፥ ቀበተተ። 2. መታ፥ ደበደበ።

ቀብዳዳ (ቀበደድ) ቅ ዘርጣጣ፥ ሆዱ የተነፋ።

ቅብድድ ዝ.ከ.

ተንቀበደደ ግ ሆዱ ገፋ፥ ተነፋ፥ ተንዘረጠጠ።

አንቀበደደ ግ አንዘረጠጠ፥ ነፋ፥ አሳበጠ (ሆድን)።

እንቅብድ ቅ ዘርጣጣ፥ ሆደ ትልቅ።

ቀበጠ ግ 1. ተቀናጣ፥ ባለጌ፥ ማድረግ የማይገባውን ነገር አደረገ። 2. (ዘይ.) ምቾት አገኘ፥ ዘበነ። *የቀበጠ ጌታ።*

ቀበጢና ቅ ቀበጥ።

ቀበጥ ቅ 1. ቅልብልብ፥ ከልፋልፍ። 2. እረፍት ቢስ፥ ማድረግ የማይገባውን የሚያደርግ። 3. ቅንጡ።

የቀባጭ ስ አያገባው ገብቶ የተናገረ ወይም የሰራ የሚከፍለው መቀጫ።

ቅብጠት ስ 1. በመቀናጣት የሚፈፀም ተገቢ ያልሆነ ድርጊት። 2. ልፊያ።

ቅብጥብጥ (ቀበጥባጣ) ቅ 1. ቀንጥንጥ፥ እርፍ የማይቀመጥ፥ ቅልብልብ። 2. ብስጩ፥ ነጭናጫ። *ህፃኑ ከመታመሙ የተነሳ ቅብጥብጥ ሆነ።* 3. (ዘይ.) ዘበናይ፥ ቅንጡ።

ተቃበጠ ግ ተላፋ፥ ተዳራ።

አቀበጠ ግ ቀበጥ አደረገ፥ አሞላቀቀ።

ተቅበጠበጠ ግ 1. ተቁነጠነጠ፥ ተወራጨ። 2. አመለ ቢስ ሆነ፥ ተበሳጨ፥ ተነጫነጨ።

አቅበጠበጠ ግ 1. አቁነጠነጠ፥ አወራጨ። 2. አበሳጨ፥ አነጫነጨ።

ቀቢፀ ተስፋ ስ ተስፋ መቁረጥ።

ቀባ ግ 1. አንድን ነገር ለማራስ፥ ለማለስለስ፥ ለማወዛት፥ መልክ ለመስጠት፥... በቅባት ወይም በቀለም፥...ለቀለቀ፥ አበሰ። 2. የንጉሥነት ወይም የነቢይነት ወይም የክህነት፥... ሥልጣን ሰጠ፥ ወይም የተፀለየበትን ቅባት በመቀባት ባረከ። 3. (ዘይ.) ሃጢአተኛ፥ በደለኛ አስመሰለ፥ ስም አጠፋ። *ስሙን ቀቡት።*

ቅባት ስ 1. ከስብ፥ ከወተት ወይም ከሌሎች ነገሮች የሚገኝና ዘይትን፥ ቅቤን፥ ሞራን፥ ቅልጥምን የመሳሰለ ሁሉ። 2. ከዘይት፥ ከስብ፥ ... ነገሮች ጋር ተቀምሞ በፈሳሽ ወይም በጭቃ መልክ የሚሰራ መድሃኒት ወይም የሰውነት ቆዳን፥ ፀጉርን ማበሻ፥ ማለስለሻ፥ ማውዣ።

የቅባት እህሎች ስ እንደ ኑግ፥ ሰሊጥ፥... የመሳሰሉና ዘይት ሊወጣቸው የሚችል የእህል አይነቶች።

ቅቤ ስ ከወተት የሚገኝ ቅባት።

ቅቤን አንገሰ ቅቤን አንጥሮ ለረዥም ጊዜ አቆየ።

ቅቤው በሰለ ቆየ፥ ጠነከረ።

ቅቤ አንጓች/ጠባሽ እውደድ ባይ፥ አድር ባይ፥ አሽቃባጭ፥ አዛኝ መሳይ።

የቅቤ ቅል ስ 1. ቅቤ መያዣ፥ ማስቀመጫ። 2. (ዘይ.) አዘውትሮ ቅቤ የሚቀባ።

የቅቤ ቅል መሰለ ወዛም ሆነ፥ ወዙ ተቅለጠለጠ።

የቅቤ እር ስ ቅቤ ተነጥሮ ሲጠለል ከስሩ የሚቀረው ዝቃጭ፥ አተላ።

ቅብ ቅ የተቀባ። *ወርቅ ቅብ ሰአት አለኝ።*

ቅብአ መንግስት ስ ንጉስ ወይም ንግስት ዘውድ ሲጭኑ (ሲነግሱ) በቤተክህነት ሰዎች የሚቀቡት የተፀለየበት ቅባት (ዘይት)።

ቅብአ ቅዱስ (ቅባቅዱስ) ስ ከወይራ ፍሬ የሚዘጋጅ የተፀለየበትና ህዋናት ከርቤትና

ሲነሱ፥ ታቦት በሚባረክበት እለት የሚቀቡት ዘይት። ቅብአ ሜሮንም ይባላል።

ቅብአ ኑግ (ቅባኑግ) ስ ከኑግ የሚወጣ ቅባት፥ ዘይት።

ቅብአክህነት ስ የቤተክርስቲያን አገልጋዮች ስልጣነ ክህነት በሚቀበሉበት ጊዜ የሚቀቡት የተፀለየበት ቅባት (ዘይት)።

ተቀባ ግ የነቢይነት ወይም የክህንነት፣...ስልጣን ተቀበለ፥ ተሾመ ወይም የተፀለየበትን ቅባት በመቀባት ተባረከ።

ተቀብኦ ስ ተሰጥኦ።

ተቀባባ ግ 1. ተነካካ፥ ተዳረሰ፤ እርስ በርስ አንዱ ባንዱ ላይ ሳከከ (ነገርን)።

ቀባ (ቃባ) ስ በዋሻ ወይም በገደል ወይም በውስጠ ክፍት ግንድ ውስጥ የሚገኝ ማር ከነንቡ።

ቀባቆራጭ ስ የቀባ ማር የሚቆርጥ ሰው።

ቀባሪ "ቀበረ" ስር ተመ.

ቀባዠረ(ቀባጀረ) ግ ቀባጠረ፤ ዘባረቀ፤ የሆነ ያልሆነውን ተናገረ።

ቀባዣሪ ቅ (ስድብ) ቀባጣሪ፥ ዘባራቂ፤ የሆነ ያልሆነውን የሚናገር።

አስቀባዠረ ግ አስቀባጠረ፥ አስዘባረቀ፤ የሆነ ያልሆነው አናገረ።

ቀባጠረ ግ የሆነ ያልሆነውን ተናገረ፥ ለፈለፈ።

ቀባጣሪ ቅ (ስድብ) የሆነ ያልሆነውን የሚናገር፥ ለፍላፊ።

አስቀባጠረ ግ የሆነ ያልሆነውን አናገረ፥ አስለፈለፈ።

ቀብራራ "*ቀበረረ" ስር ተመ.

ቀብር "ቀበረ" ስር ተመ.

ቀብቃባ "*ቀበቀበ" ስር ተመ.

ቀብታታ "ቀበተተ" ስር ተመ.

ቀብዳዳ "ቀበደደ" ስር ተመ.

ቀብድ (ቃብድ) ስ እቃን ለመግዛት ወይም ለማሰራት በቅድሚያ የሚከፈል ገንዘብ፤ መያዣ።

ቀተረ^{1} ግ ነፋ፥ አሳበጠ፥ ቀበተተ፤ ወጠረ። *የቂል በትር ሆድ ይቀትር።*

ቅትር ቅ የተነፋ፥ ያበጠ፥ ውጥር።

ተቀተረ ግ ተነፋ፥ ተወጠረ፥ አበጠ፥ ተቀበተተ።

ቀተረ^{2} ግ ቀረቀረ፤ ሸገረ።

ቅትርት ስ ሞፈሩንና በሞፈሩ ግራና ቀኝ ያሉትን ድግሮች አጣምሮ እንዲያያይዝ በተጠቀሱት እቃዎች ቀዳዳ ውስጥ የሚሰካ ቀጭን እንጨት(ስእሉን ሞፈር ስር ተመ.)።

ተቀተረ ግ ተቀረቀረ፥ ተሸገረ።

ቀተረ^{3} ግ ገተረ፤ ቀሰረ፥ አቆመ።

ተቀተረ ግ ተገተረ፤ ተቀሰረ፥ ቆመ።

*ቀተረ

ተቀታተረ ግ ተወዳደረ፤ ተፎካከረ፥ ተከራከረ። *ከበለቀትር አትቀታተር።*

አቀታተረ ግ አወዳደረ፤ አፎካከረ፥ አከራከረ። *ያለአቅሙ ምን አቀታተረው።*

ቀትር^{1} ስ ቁመና፥ የሰውነት ቅርፅ።

ቀትረ ቀላል ቅ ቁመን ያለና ለአይን ጎላ ብሎ የማይታይ (ሰው)።

ቀትር^{2} ስ እኩለ ቀን፤ የቀን አጋማሽ።

የቀትር እባብ ስ 1. አደገኛ፤ መርዘኛ እባብ። 2. (ዘይ.) በጣም ተንኮለኛና መርዘኛ የሆነ (ሰው)።

ቀነሰ ግ 1. አሳነሰ፤ አጎደለ፤ ከላዩ ላይ አነሳ፤ ዝቅ አደረገ (ብዛትን፤ ክብደትን፤ ቁመትን፤ መጠንን)። 2. ቀድሞ ከነበረው አነሰ፤ መነመነ፥ ዝቅ አለ፥ ጎደለ። *ኪታመመ ወዲህ ሰውነቱ ቀነሰ።* 3. በረድ አለ፥ ታገሰ፥ ሻል አለ (ህመሙ፤ ንዴቱ፤...)። 4. ዝቅ አደረገ፤ አረከሰ (ዋጋን)። 5. ቀድሞ ከነበረው በታች ሆነ፥ ረከሰ (ዋጋ)። 6. ዝግ አደረገ (ፍጥነትን)። 7. ዝግ አለ(ፍጥነት)።

መቀነስ ስ ከተወሰነ ቁጥር ወይም መጠን ላይ የተወሰነ ቁጥር ወይም መጠን በማንሳት የሚሰራ የሂሳብ ስሌት መንገድ፤ ከአራቱ የስሌት መደቦች አንዱ።

መቀነሻ ስ ከአንድ ነገር ላይ እያነሱ ወደሌላ መገልበጫ፥ ማዛወሪያ እቃ፤ ማቀናነሻም ይባላል። ለምሳሌ ከጋን የሚቀነስ ጠላ የሚቀመጥበት እንስራ ወይም ገንቦ።

ቅናሽ ስ 1. አነስተኛ ወይም ርካሽ ዋጋ። *በቅናሽ የተገዛ እቃ ነው።* 2. ጠላ ሲሞላ ከላዩ ተቀንሶ የቀረ፤ ሰለሊታ።

ቀናነሰ ግ ከዚህም ከዚያም ቀነሰ፤ አነሳ።

ቅንስናሽ ስ ጋን ሲሞላ ተቀንሶ የቀረ፤ የተረፈ ጠላ።

ቅንስናሽ ገንዘብ ስ ዝርዝር፥ ሽርፍራፊ ገንዘብ።

ተቀነሰ ግ ከተወሰነ መጠን ወይም ቁጥር ላይ ተነሳ፤ ዝቅ አለ።

ተቀናሽ ቅ ከተወሰነ መጠን ወይም ቁጥር ላይ የሚቀነስ ወይም የሚነሳ።

ተቀናነሰ ግ ተቀነሰ።

ተቀናናሽ ሂሳብ ስ ከተለያዩ መጠኖች ላይ ተቀንሶ የቀረ ሂሳብ።

አቀናነሰ ግ ቀነሰ፤አንዱን ከአንዱ ላይ አነሳ ።

ማቀናነሻ "**መቀነሻ**" ን ተመ.

ቀነቀነ^1 ግ 1. ነቀዘ፡ ጠነጠነ። 2. በዓ፥ አሳከከ።

ቅንቅን ስ 1. ነቀዝ፡ የእንጨት፥ የእህል ትል። 2. በጣም ትንንሽ የሆነ ቅጫም መሰል ተባይ (ብዙውን ጊዜ ዶሮ ላይ የሚገኝ)።

ቅንቅናም ቅ (ስድብ) 1. ቅንቅን ያለበት፥ የበዛበት። 2. (ዘይ.) ስስታም፡ ንፉግ፡ ቆንቋና።

ቀነቀነ^2 ግ መረመረ፡ ፈተሸ፡ ፈተነ።

ቅንቀና ስ 1. ምርመራ፥ ፍተሻ (ለጥናትና ምርምር ተግባር የሚያደረግ)። 2. ዜማ ማውረድ።

አቀነቀነ ግ 1. አዜመ፤ ዘፈንን አወረደ። 2. አራመደ (አሳማን፡ ሃሳብን)።

አቀንቃኝ ስ 1. የዜማ፡ የዘፈን፡... አውራጅ። ቅ 2. አንድን አላማ አራማጅ።

ቀነበረ ግ በእሳት፥ በፀሃይ ተንቃቅቶ ደረቀ፤ ጠና፡ በሰለ (እንጀራ፥ ዳቦ)።

*ቀነበረ

ቅንብር ስ አንዱ ከአንዱ ጋር እንዲጣጣም፡ አብሮ እንዲሄድ አድርጎ የማስተካከል ስራ ወይም ውጤት፤ ቅንጅት፡ ጥንቅር። *የሙዚቃ ቅንብር።*

ተቀናበረ ግ ተቀናጀ፥ ተጠናቀረ፡ አንዱ ከአንዱ ጋር እንዲጣጣምና አብሮ እንዲሄድ ሆኖ ተዘጋጀ፤ ተደራጀ።

ተቀነባበረ ዝ.ከ.

አቀናበረ ግ አቀናጀ፤ አጠናቀረ፥ አንዱ ከአንዱ ጋር እንዲጣጣምና አብሮ እንዲሄድ አድረጎ አዘጋጀ፥ አደራጀ።

አቀናባሪ ቅ አዘጋጅ። *ዜማ አቀናባሪ።*

አቀነባበረ ግ አቀናበረ።

ቀነበበ ግ ከበበ፡ ክብ አደረገ።

ቅንብብ ቅ መሃሉን ትቶ ዙሪያውን የተላጨ (የራስ ፀጉር ወይም ራስ)።

*ቀነተ

መቀነት ስ ከፈትል የተሰራ የሴቶች የወገብ መታጠቂያ።

መቀነቷን ፈታች በልጃገረድነት የመጀመሪያ ባል አገባች።

መቀነትማ ቅ የሆዱና የጀርባው መካከለኛ ዙሪያ መቀነት የሚመስል ቅርፅ የያዘ ነጭ መስመር ያለበት (ፍየል)።

መቀነቻ ስ 1. መታጠቂያ፥ ወገብ ማሰሪያ ቀበቶ፥ ሰቅ፥...። 2. ኮርቻ ወደ ግራና ቀኝ እንዳይዋልል አጥብቆ የሚይዝ፥ በፈረስና በበቅሎ ሆድ ላይ የሚታሰር ዘለበት ያለበት ጠፍር(ስእሉን ኮርቻ ስር ተመ.)።

ቅናት ስ 1. ሰቅ፥ ቀበቶ፥ መታጠቂያ። 2. መነኩሴዎች፡ ባህታዊዎች፥... ወገባቸውን ጠልፈው በአንገታቸው የሚያጠልቁት፥ በደረት በኩል መስቀልኛነት ያለው ሰንሰለት ወይም ጠፍር።

ቀነዘረ ግ 1. ፈጥኖ ደረሰ፥ ያለጊዜው አደገ፥ ፋፋ (ተክል፡ አዝመራ፥...)። 2. ሴሰነ፥ በአንድ ሴት የማይረጋ፤ የማይወሰን ሆነ።

ቅንዝር ስ ከፍ ያለ የዝሙት፥ የፍትወት ስሜት።

ቅንዝረኛ ቅ (ስድብ፡ ነውር) ሴሰኛ፥ ዘማዊ፥ አመንዝራ።

*ቀነዘነዘ

ቅንዝንዝ (ቀነዝናዛ) ቅ (ስድብ) አርፎ፥ ረግቶ የማይቀመጥ።

ቅንዝንዝ አለ ግ ተቅነዘነዘ።

ቅንዝንዝ አደረገ ግ አቅነዘነዘ።

ተቅነዘነዘ ግ ተንቀዠቀዠ፤ አረፍት፡ እርጋታ አጣ።

አቅነዘነዘ ግ አንቀዠቀዠ፤ እረፍት፡ እርጋታ ከለከለ።

ቀነዘፈ ግ 1. ቆረጠ፡ ቀነጠሰ፡ ዘነጠፈ፥ ገነጠለ (የተክልን፥ የዛፍን ቅርንጫፍ)።

ቅንዛፊ ስ የዛፍ ምልማይ፥ ግንጣይ።

ቅንዝፍ ቅንዝፍ አለ ግ ዱብ ዱብ አለ፤ ወረደ(እንባ)።

ተቀነዘፈ ግ ተቀነጠሰ፤ ተገነጠለ፡ ተዘነጠፈ።

ቀነዝናዛ "*ቀነዘነዘ" ስር "**ቅንዝንዝ**" ን ተመ.

ቀነደለ ግ 1. ቀነደበ፥ በጣ፥ ቀረጠ (ቅንድብን)። 2. መታ፥ ደበደበ።

ቅንድል ቅ የተቀነደለ፡ የተቀነደበ፥ የተበጣ (ቅንድብን)።

ተቀነደለ ግ ተበጣ፡ ተቆረጠ፡ ተቀነደበ።

*ቀነደረ

ተሽቀነደረ ግ 1. የኩራት አለባበስና አካሄድ አሳየ። 2. ተቀናጣ፤ ዘለለ (በደስታ)።

አሽቀነደረ ግ አቀናጣ፤ አዘለለ (በደስታ)።

ቀነደሸ ግ 1. ሰበረ፡ አንከተ፡ መታ፡ ቀነደበ (ራስን፥ ቀንድን፥ ቅንድብን)። 2. አረጀ፡ ተንቋቋ፡ ጎበጠ።

ቅንዳሻም ቅ (ስድብ) ያረጀ፤ የጎበጠ (ሰው)።

ቀነደበ^1 ግ 1. ቅንድብን፥ የአይንን ቆብ በጣ። 2. አናትን፥ ቀንድን፥...መታ። 3. ቅንድብን ላጨ፡ ነቀለ።

መቀንደቢያ ስ ቅንድብን እየነቀሉ የሚፈለገውን ቅርፅ እንዲይዝ ለማድረግ የሚያገለግል የውበት እቃ።

መቀንደቢያ

ቅንድብ ስ ከአይን በላይ አግድም የሚበቅለው ፀጉር ወይም ፀጉሩ የሚበቅልበት ቦታ። በአይን ቆብ ወይም በአይን መሸፈኛ (ክዳን) ጠርዝ ዙሪያ ያለውም ፀጉር ቅንድብ ይባላል(ስእሉን አይን ስር ተመ.)።

ቀንደበ² ግ በጉጉት ጠጣ። *ላንድ ብርሌ ጠጅ ቀንደበና ሄደ።*

ቀንጻ ግ ደረቀ፣ ከረረ። *እገሌ ወገቡ ቀንጽቶ ጎንበስ ቀና ማለት አቅቶታል።*

ቀንጻ ቀንጻ አለ ፈጠን ፈጠን ብሎ ተራመደ፣ ሄደ፣ ተሽቀነጠረ። 2- ቀደም ቀደም አለ (በአነጋገር)።

አቀንጻ ግ 1. አደረቀ፣ አከረረ። 2. መታ (በሃይል)።

***ቀነጀ**

መቀናጆ ስ ከሌላ ሰው በሬ ጋር እየተጣመረ የሚያርስ አንድ በሬ፣ አጣማጅ።

ቅንጅት ስ 1. ዝግጅት፣ ቅንብር፣ ጥንቅር። 2 ግንኙነት፣ ጥምረት።

ተቀናጀ ግ 1. ተጣማጅ ወይም አጣማጅ አገኘ፣ ከሌላ በሬ ጋር ተጎዳኘ፣ ተጣመደ። 2. ተጣመረ። 3. ተቀናበረ፣ ተስተካከሉ፣ ተዘጋጀ።

አቀናጀ ግ 1. አንዱን በሬ ከራሱ፣ ሁለተኛውን ከሌላ አምጥቶ ጠመደ። 2. አጣመረ። 3. አቀናበረ፣ አስተካከሉ፣ አዘጋጀ።

***ቀነጠረ**

ተሽቀነጠረ ግ በሃይል ርቆ ተወረወረ፣ ተስፈነጠረ።

አሽቀነጠረ ግ አርቆ በሃይል ወረወረ፣ ጣለ።

ቀነጠሰ ግ 1. በጠሰ፣ ቆረጠ፣ ጎመደ። *ላንገቱን በጎራዴ ቀነጠሰው።* 2. የጎመንን፣ የሳማን ቅጠል ከግንዱ፣ የበርበሬን ዛላ ከቂንጹ እየለየ ቆረጠ፣ ቀነጠበ።

ቅንጥስ አለ ግ 1. በአጭር ተቀጨ፣ ሞተ። 2. ተቀነጠሰ።

ተቀነጠሰ ግ ተቆረጠ፣ ተቀነጠበ።

ቀነጠበ ግ 1. በትንሹ ቆረጠ፣ ከጫፍ ቀነጠሰ። 2. በጥቂቱ ወሰደ፣ አነሳ።

መቀንጠቢያ ስ በጥጥ መንደፊያ(ደጋን) ላይ የተወጠረን ጅማት ለማንዘር የሚያገለግል የቅል እንገት ቁራጭ(ስእሉን ደጋን ስር ተመ.)።

ቅንጣቢ ስ በልኳንዳ ቤቶች ውስጥ ከየብልቱ በትንሽ በትንሹ ተቆርጦ የተጠራቀመ ቁርጥራጭ ስጋ።

ተቀነጠበ ግ ከጫፉ ላይ በትንሹ ተበጠሰ፣ ተቆረጠ።

ተቀነጣጠበ ግ ተቆራረጠ፣ ተበጣጠሰ፣ ተቀነጣጠሰ።

ቀነጣ ግ ኮራ፣ ራሱን ከፍ ከፍ አደረገ፣ ታበየ።

ቅንጡ ቅ ቀብራራ፣ ቅምጥል።

ቅንጦት ስ 1. ከመጠን ያለፈ ድሎት፣ ምቾት። 2. የመንቀባረር፣ የመንደላቀቅ ሁኔታ።

የቅንጦት እቃ ስ ለህይወት ወይም ለኑሮ እጅግም አስፈላጊ ያልሆነና ድሎት፣ ምቾት ለማግኘት ሲባል የሚገዛ ውድ እቃ።

ቅንጦተኛ ቅ ደልቃቃ፣ ቀብራራ።

ተቀናጣ ግ 1. ተቀማጠለ፣ ተኩራራ፣ ቀበጠ። 2.ከሚያስፈልገው በላይ (የማይችለውን፣ የማይገባውን) ላድርግ አለ።

አቀናጣ ግ 1. አቀማጠለ፣ አኩራራ፣ አንደላቀቀ። 2. አቀበጠ።

ቀነጨረ ግ 1. ሳያድግ፣ ሳይፋፋ ባለበት ጠና፣ ጠነከረ፣ ከረረ። 2. ደረቀ፣ ጠነከረ። *ቆሎው ቀንጭሯል።*

ቀንጫራ (ቅንጭር) ቅ ሳያድግ፣ ሳይፋፋ የቀረና በዚያው ባለበት ሁኔታ የጠነከረ፣ የከረረ፣ ድባቅ።

ቀነጨበ ግ 1. ቆነጠረ፣ ቆንጥሮ ወሰደ። 2. በገበጣ ጨዋታ ላይ ጀማሪ ሆኖ፣ የጀመረውን ዙር ተጫወተ።

ቅንጨቢ ስ የተቆነጠረ፣ የተቀነጨበ ጥቂት ነገር።

ቀነፈ ግ 1. የልብስን ጫፍ ዳር ዳሩን አጥፎ፣ ቀልብሶ ሰፋ። 2. የቅንፍ ምልክት አኖረ።

ቅንፍ ስ 1. የተቀነፈ፣ ወደላይ ታጥፎ ተቀልብሶ የተሰፋ ክፈፍ። 2. አንዱን ከሌላው ለመለየት፣ በአማራጭነት ለማስቀመጥ፣ ለማብራራት፣... ከአንድ ፊደል፣ ቃል ወይም አረፍተ ነገር ግራና ቀኝ የሚቀመጥ ደጋንማ ምልክት፣ ምልክቱም " ( )" ነው።

ቅንፋት ስ እጥፋት፣ ቅልብሳት።

ቀና¹ ግ 1. ተመቀኘ፣ ሌላው ባደረገው ወይም ባገኘው ተከፋ፣ ተናደደ። 2. ሌላው ያገኘውን መልካም ነገር በማየት ለራሱም ተመኘ። 3. የትዳር ጓደኛን ወይም ፍቅረኛን እንጠቃለሁ፣ አጣለሁ ወይም ከሌላ ጋር የፍቅር ግንኙነት

ይኖራል በሚል ስጋት የንዴት፥ የብስጭት፥ የመብከንከን ስሜት ተሰማው።

ቀናተኛ ቅ 1. ምቀኛ፤ ሌላው ባደረገው ወይም ባገኘው የሚከፋ፥ የሚናደድ። 2. የሚቆጭ፥ የሚቆረቆር። *የኢትዮጵያ ህዝብ ለሃገሩ ነፃነት ቀናተኛ ነው።* 3. የቅናት ስሜት ያለበት።

ቅናት ስ 1. የምቀኝነት ስሜት፤ ሌላው ባለው፥ በሚያገኘው ወይም በሚያደርገው መከፋት፥ መናደድ። 2. በሌላው መልካም ነገር የመደሰትና ለራሱም የመመኘት ስሜት።3. የትዳር ጓደኛን ወይም ፍቅረኛን አጣለሁ፤ እነጠቃለሁ፥...በሚል ስጋት የሚፈጠር የብስጭት፥ የመከፋት፥ የንዴት ስሜት ወይም አድራጎት።

ቅናተኛ ቅ የቅናት ስሜት ያለበት።

አስቀና ግ 1. ለቅናት መነሻ ምክንያት ሆነ፤ ወደ ቅናት ገፋፋ። 2. ያደረገው ወይም የተደረገው፤ የተሰራው መልካም ነገር በሌላው ላይ የበጎ ቅናት ስሜት አሳደረ፥ አጓጓ፤ አተጋ።

ቀና^2 ግ 1. ቀጥ አለ፤ ረታ (የጎበጠው፥ የተጣመመው)። 2. ቀጥ አለ፥ ቆመ፤ ተነሳ (ተጋድሞ የነበረው)። 3. ተሳካ፥ ተከናወነ፤ ሰመረ። *የሄድክበት ቀናኽ*። 4. በመታረስ ወይም መኖሪያ በመሆን እንዲያገለግል ተደረገ፥ ለማ (ቦታ)። 5. እርሻ ለመደ፥ ተማረ፥ ሰላ፥ ተንከባከበ (ወይፈን)። 6.ገባ፥ ሰረፀ። *ትምህርቱ ቀናው* ። 7. አሻረ፤ አዳነ። *ስለው ቀናው*። 8. ተስተካከለ፤ ታረመ።ቅ 9. ገር፤ የዋህ። 10. ምቹ፥ ቀላል። 11. ጥሩ፤ ደግ፥ ተንኮል የሌለበት (*ለአስተያየት ወይም ለአስተሳሰብ*)። 12. አስቸጋሪ ያልሆነ፤ ጠማማነት የሌለው፥ ቀጥታ የሆነ።

ቀና (በቀና/ቀና ለቀና አንፃር ለአንፃር፥ ፊት ለፊት። *ቀና በቀና ተናገረ።*

ቀና አለ ግ 1. ቀጥ አለ (ጎብጦ፥ ተጣሞ የነበረው)። 2. እንደመቆም፤ እንደመነሳት አለ (ተጋድሞ የነበረው)።

ቀና አደረገ ግ አቀና፥ ቀጥ አደረገ (ጎብጦ የነበረውን)። 2. እንደማቆም እንደማንሳት አደረገ (ተጋድሞ የነበረውን)።

ቅናት ስ የድምፅን ተነሽነት የሚያሳይ የያሬዳዊ ዜማ ምልክት።ምልክቱም(ʕ)ነው።

ቅን ቅ 1. ደግ፤ ገር፥ ክፋት፥ ተንኮል የሌለው (ሰው)። 2. ጥሩ፤ ገር የሆነ፤ ክፋት የሌለው (ሃሳብ፤ አስተያየት)።

ቅኝ [ግዛት] ስ በሌላ አገር መንግስት የተወረረና በወራሪው መንግስት ቁጥጥር ስር የሚተዳደር፥ ነፃነቱን ያላገኘ አገር።

ቅኝ አገዛዝ ስ ሌላን አገር በመውረር የብዝበዛና የጭቆና አስተዳደር የሚካሄድ ፖሊሲ።

ቅኝ ገዢ ስ ሌላን አገር በወረራ በመያዝ በቁጥጥር ስር አድርጎ የሚያስተዳድር መንግስት።

ተቃና ግ 1. ቀጥ እንዲል ተደረገ (ጎብጦ፥ ተጣሞ የነበረው)። 2. ተሳካ፥ ሰመረ። *ሂደቱ ተቃና።*

አቀና ግ 1. ሸጠ (እህልን)። 2. አቅጣጫ ያዘ፥ አመራ። *ፊቱን ወደ ሰሜን አቀና።* 3. ለመኖሪያ፥ ለእርሻ፥ ለአስተዳደር ምቹ እንዲሆን አደረገ፤ አለማ (ቦታን፥ አገርን)።

አቅኚ(አቅኝ) ቅ አልሚ (አገርን፤ ቦታን)።

አቃና ግ 1. ቀጥ አደረገ (ጎብጦ፥ ተጣሞ የነበረውን)። 2.አሳካ፥ አሳመረ፥ ጥሩ አደረገ። *ሂደቱን ሊቃናለት*። 3. አስተካከለ፥ አረመ።

ቀናተኛ "**ቀና**^{1}" ስር ተመ.

ቀናነስ "**ቀነሰ**" ስር ተመ.

ቀን ስ 1. (ብ.ቁ. **ቀናት**) ሃያ አራት ሰአታት የሚሆን የብርሃንና የጨለማ ጊዜ። *አንድ አመት ሶስት መቶ ስልሳ አምስት ቀናት አሉት*። 2. ከጠዋት እስከ ማታ ያለው የብርሃን ጊዜ። *ቀን ቀን ለየተግባራችን ማታ ማታ ከድንኳን እናድር ነበር*።3. ወቅት፥ ጊዜ። *ያጣም ያገኝና ያገኘም ያጣና ያስተናግዳል ይሄ ቀን ያልፍና*። 4. ሰአት፤ ጊዜ። *ቀኑ እንዴት ይርቃል?* 5. የተወሰነ፤ የተጠበቀ ጊዜ፥ ቀጠሮ። *ቀኑ ደርሶ ነው የሞተው /የመውለጃዋ ቀን ደርሷል።*

ቀኑ ስንት ነው? የወሩ ስንተኛው እለት ነው?

ቀኑ ነደደ የእለቱ የፀሃይ ሙቀት በረታ፥ አየለ፤ ቃጠሎ ሆነ።

ቀኑ ከበደ ደመና ሆነ፤ ጨፈገገ፥ ሰማዩ ጠቆረ።

ቀኑ ደረሰ የመሞቻው፥ የመጥፊያው ጊዜ ተቃረበ፥ መጣ።

ቀን ሆነ ረፈደ፥ ወደእኩለ ቀን ተጠጋ።

ቀን ሰጠ 1. ጊዜን በማራዘም ፋታ ሰጠ። 2. ጊዜው፥ ወቅቱ አመቸ፤ የፈለጉትን ለማድረግ አስቻለ።

ቀን ቆረጠ ጊዜ፥ ቀጠሮ ወሰነ።

ቀን ወጣ 1. የችግር ጊዜ አልፎ የብልፅግና፥ የጥጋብ ጊዜ ተተካ። 2. ዝናቡ ቆመ፥ ፀሃይ ወጣ፥ ብራ ሆነ።

ቀን ወጣለት ከችግር ተገላገለ፥ አለፈለት፥ ተመቸው።

ቀን ጎደለበት የመከራ፥ የአደጋ፥ የችግር ቀን ሆነበት፥ አደጋ አጋጠመው።

ቀነ ጎደሎ (የቀን ጎደሎ) ለአደጋ፥ ለመከራ የሚዳርግ መጥፎ አጋጣሚ የሚያጋጥምበት ቀን።

ቀን ጣለው ደሀየ፥ ተቸገረ (ቀድሞ ሃብታም የነበረው)።

ቀኗ ደረሰ የመውለጃዋ ጊዜ ተቃረበ።

ቀን ለቀን ተው.ግ. በቀን፥ ብርሃን ባለበት ጊዜ።

ቀን በቀን ተው.ግ 1. ሁል ቀን፥ ሁልጊዜ። 2. በቀን፥ ብርሃን ባለበት። *ቀን በቀን ሌባ ከቤቱ ገብቶ ዘረፈው።*

ቀነ ቀጠሮ ስ የቀጠሮ እለት (የፍርድ ቤት፥...)።

ቀን መቁጠሪያ ስ የአመቱ ወራትና ቀናት የሚውሉባቸውን እለታት ለመቁጠርና ለመለየት የሚያስችል ሰሌዳ፥ ሰንጠረዥ።

የቀን ሰራተኛ/ሙያተኛ ስ በቋሚነት የተቀጠረበት ስራ የሌለውና በቀን ክፍያ የሚያገለግል የጉልበት ሰራተኛ፤ ሸቃይ፤ ኩሊ።

የቀን ተማሪ ስ ቀን ቀን በመደበኛ የትምህርት ሰአት ትምህርቱን የሚከታተል ተማሪ።

የቀን ጅብ ምህረት የለሽ፥ ጨካኝ፥ እናት አይምሬ (ያገኘውን ከመንጠቅ፣ ከመብላት፥ ከመግደል የማይቆጠብ)።

ቀነኛ (የቀንኛ) ስ (በገጠር አካባቢ የሚባል) ምሳ።

ቀንበር (ቀምበር) ስ በእርሻ ጊዜ በሁለት በሬዎች ትከሻ ላይ የሚያርፍና ከሞፈሩ ጋር በምራን የሚያያዝ የግብርና እቃ(ስእሉን ሞፈር ስር ተመ.)።

ቀንበር ተሸከመ መከራ፣ ስቃይ ተቀበለ።

የ--ቀንበር የ -- ሸክም፥ ጫና። *የበረንት ቀንበር።*

ቀንበጥ(ቀምበጥ) ስ በጣም ለምለም የሆነው ቅጠል የሚገኝበት የዛፍ ወይም የተክል ጫፍ፥ እምቡጥ።

ቀንዘል ስ የዛፍ፥ የተክል ቅርንጫፍ።

ቀንደኛ "ቀንድ" ስር ተመ.

ቀንዲል ስ መቅረዝ።

ቀንድ ስ በእንስሳትና በአራዊት ራስ ላይ ሹል ሆኖ የሚበቅል ጠንካራ አካል።



ቀንድ

ቀንዱን አለው 1. በቁጣ፥ በስድብ፥... ዝም አሰኘው፣ አሳፈረው። 2. አናቱን፥ ጭንቅላቱን መታው፥ ቀነደበው።

ቀንደ መለከት ስ ከቀንድ የተበጀ መለከት።

ቀንድ አወጣ /አበቀለ ተናደደ።

ቀንድ አውጣ (ቀንዳውጣ) ስ ሌብሱ የዛጎል አይነት የሆነ፥ እየተሳበ የሚሄድ፥ ለስላሳ አካል ያለው፣ በክረምት በብዛት የሚታይ ትል።

ቀንድ አውጣ

የቀንድ ከብት ስ የበሬና የላም አጠቃላይ ስም። እንደ በሬና ላም ያሉትን እንስሳት ከጋማ ከብቶች ለመለየት የሚያገለግል ስም።

የቀንድ ዋንጫ ስ ከቀንድ የተበጀ ዋንጫ።

ቀንደኛ ቅ ዋነኛ፥ ግንባር ቀደም (በአብዛኛው ለመጥፎ ድርጊት)።

ቀንዳም ቅ ቀንዱ ረጅም የሆነ (በሬ፥...)።

ቀንጃ "*ቀነጀ" ስር ተመ.

ቀንጠልባ ቅ ለፍላፊ፥ ቀባጣሪ፥ ወሬኛ።

ቀንጠፋ ስ መጠኑ አነስተኛ የሆነ፥ እሾህ ያለው የእፀዋት አይነት።

ቀንጠ "ቈንጠ[1]" ን ተመ.

ቀንጨራ "ቀነጨረ" ስር ተመ.

ቀኖት ስ የብረት ችንካር፤ ምስማር።

ቀኖና ስ 1-(ክር.) ሱባኤ። 2- ህግ፥ ደንብ፥ ስርአት (የቤተክርስቲያን)። 3 የማይለወጥ፥ የማይሻሻል ህግ፥ ደንብ፥ መመሪያ (ፍልስፍና)።

ቀኖና ያዘ ሱባኤ ገባ።

***ቀኘ(ቀነየ)**

ቅኔ ስ 1. የተለያዩና የተወሰኑ የዜማ ምጣኔዎች ያሉት፣ እንደ ግጥም ቤት የሚመታ፣ ይዘቱ ውበትና ጥልቅ ምስጢር እንዲኖረው ተደርጎ በልዩ ልዩ የቅኔ መንገድ አይነቶች የሚቀናበርና በትምህርት አማካይነት የሚቀሰም ስነ ቃላዊ ድርሰት። 2. ምስጢር አዘል ንግግር።

ቅኔ ሰጠ ለምስጋና፥ ለአከባበሮት፥... የሚሆን ቅኔ አበረከተ።

ቅኔ ቆጠረ 1. ቅኔ አዘጋጀ። 2. ቅኔ አወቀ፥

ተማረ (በመጠኑ)።

ቅኔ ነጠቀ ባለቅኔው አዘጋጅቶ በማሰማት ላይ ካለው ቅኔ ውስጥ ድንቁን ክፍል (ሰንኝ) ሌላው አድማጭ ቀድሞ ተናገረ፣ ሞላ።

ባለቅኔ ቅኔ የሚያውቅ፡ የተማረ።

ቅኔ ማህሌት ስ በቤተክርስቲያን ውስጥ መዘምራን በመቋሚያ፣ በከበሮና በፀናፅል የሚታጀበውን የምስጋና ዝማሬ የሚያሰሙበት ክፍል።

ቅኔ ቤት ስ የቅኔ ትምህርት ቤት።

ተቀኘ ግ 1. የመጀመሪያውን ደረጃ የቅኔ ትምህርት ጨርሶና ራሱን ችሎ ቅኔ ለመድረስ ቻለ። 2. ቅኔ አዘጋጅቶ አቀረበ፣ ሰጠ፣ ተናገረ፣ አሰማ።

አስቀኘ ግ ቅኔ አስተምሮ እንዲቀኝ አደረገ።

ቀኝ ስ 1. የግራ ተቃራኒ፣ አንድ ሰው ፊቱን ወደ ሰሜን ሊያደርግ በስተምስራቅ በኩል የሚገኘው የሰውነት ክፍል፣ አቅጣጫ። 2. (ዘይ.) ምቹ፣ ቀና፡ የማያስቸግር።

ቀኞች ስ ወግ አጥባቂ ወይም አድሃሪ የፖለቲካ መስመር ተከታዮች።

[በ] ቀኝ አውለኝ በደህና፣ በሰላም አውለኝ።

ቀኛዝማች ስ 1. በጦርነት ጊዜ ከዋናው መሪ (ከፊታውራሪው) በስተቀኝ በኩል ባለው የጦር ግንባር ለሚሰለፍ የጦር አለቃ የሚሰጥ የቀድሞ ማእርግ ስም። 2. ቀደም ባለው ጊዜ ለአንዳንድ ባላባቶችና ሃብታሞች ይሰጥ የነበረ የማእርግ ስም።

ቀኝ እጅ ስ 1. በስተቀኝ በኩል የሚገኘው የሰው አንደኛው እጅ። 2. መከታ፣ መመኪያ፡ አለኝታ፣ ደጋፊ። *እሱ ቀኝ እጄ ነው።*

ቀኝ እጄን ሰጥቼሃለሁ/አውጬሃለሁ እንደኔ ሆነህ ምታልኝ፣ ደብድብልኝ።

ቀኝ ክንፍ ስ (ፖለ.) ወግ አጥባቂ።

ቀኝ ጌታ ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ) ማእርጉ ከርእሰ ደብር በታችና ከግራ ጌታ በላይ የሆነ፣ በቅኔ ማህሌት ውስጥ በስተቀኝ በኩል በመቆም ስርአቱን የሚቆጣጠር ሹም።

የቀኝ ዳኛ ስ በፍርድ ስራ ጊዜ ከመሃል ዳኛው በስተቀኝ በኩል የሚቀመጠው ዳኛ።

ቀወለለ ግ ቀውላላ ሆነ።

ቀውላላ (ቀወለል) ቅ 1. ቀጭን ረዥም። 2. ዘዋሪ፣ ወዲያና ወዲህ የሚል።

ተንቀዋለለ ግ 1. ረዘመ፣ ቀጠነ አደገ። 2. ወዲያና ወዲህ አለ፣ ዞረ፣ ያለስራ ተንከራተተ።

አንቀዋለለ ግ 1. አረዘመ፣ ቀውላላ አደረገ። 2. አንከራተተ፣ ወዲያና ወዲህ ያለስራ አዞረ።

***ቀወመ**

መቃወሚያ ስ መከላከያ።

ቅዋሜ ስ አለመስማማት፣ ተቃውሞ።

ተቃወመ ግ 1. አለመስማማቱን ገለጠ፣ ነገሩን ሳይቀበል ቀረ፣ ተቃረነ።

ተቃዋሚ ቅ 1. ተቀናቃኝ፣ ባላንጣ። 2. ተፃራሪ፣ አማራጭ ሃሳብ ያለው (ሰው)።

ተቃውሞ ስ አለመስማማት፣ ቅዋሜ።

የተቃውሞ ሰልፍ ስ አንድን ነገር፣ ሃሳብ፣ ድርጊት፣... ለመቃወም የሚደረግ ሰልፍ።

ቀወሰ ግ አበደ፣ አእምሮው ተነካ፣ ወፈፈ ሆነ።

ቀውስ ስ 1. እብድ፣ ንክ፣ ወፈፈ። 2. የነገሮች መሳከር፣ መዘበራረቅ፣ ውዥንብር።

ተቃወሰ ግ 1. ተናጋ። 2. ተምታታ፣ ተሳከረ፡ ተዘባረቀ።

አቃወሰ ግ 1. አናጋ፣ አበላሸ። 2. አምታታ፣ አሳከረ፡ አዘባረቀ።

***ቀወቀወ**

ቀውቃዋ(ቀወቀው) ቅ ከውካዋ፣ ቀጯቃጭ፣ የማያርፍ።

ቀውቀውቴ ዝ.ከ.

ተንቀወቀወ ግ ተንከወከወ፣ ተንቀገረቀገረ።

አንቀወቀወ ግ አንከወከወ፣ አንቀገረቀገረ።

ቀውላላ "ቀወለለ" ስር ተመ.

ቀውስ^{1} **"ቀወሰ"** ስር ተመ.

ቀውስ^{2} **[እሳት]** ስ በህዋር የሚወጣ የኮከብ ስም። በተጨማሪ ኮከብ ቆጠራን ተመ.

ቀውቀውቴ "*ቀወቀወ" ስር ተመ.

ቀውቃዋ ዝ.ከ.

ቀውጢ ቅ ሽብር፣ ሁከት የበዛበት አስቸጋሪ፣ ክፉ (ጊዜ)። *ቀውጢ ቀን/ ቀውጢ ዘመን።*

***ቀዘመዘመ**

ቅዝምዝም ስ ውዝግዝግ፣ ምዝግዝግ።

ተቅዘመዘመ ግ በአየር ላይ ተውዘገዘገ፣ ተምዘገዘገ (ለምሳሌ ዱላ፣ ዘንግ)።

አቅዘመዘመ ግ በአየር ላይ አውዘገዘገ፣ አምዘገዘገ (ዱላን፣ ዘንግን)።

ቀዘቀዘ ግ 1. በረደ፣ ሙቀቱን አጣ። *ቡናው ቀዘቀዘ።* 2. ብርድ ሆነ። *አየሩ ቀዘቀዘ።* 3. (ዘይ.) ቀነሰ፣ አነሰ (ጨዋታው፣ ገበያው፣ ጦርነቱ፣...)።

ቀዝቃዛ ቅ 1. የበረደ፣ የቀዘቀዘ፣ ሙቅ ያልሆነ። 2. (ዘይ.) ያልደመቀ፣ ያልተጧጧቀ።

ቀዝቃዛ ጦርነት ስ የራስን ጥቅም ለማስከበር፣ ሃይልን ለማጠናከርና አንዱ በሌላው ላይ ስጋት፣ ውጥረትና ውዝግብ ለመፍጠር፣

በመንግስታት መካከል የሚካሄድ፡ የመሳሪያ ውጊያ የሌለበት፥ ልዩ ልዩ አይነት ጥቃት፣ ዘመቻ (ድንበር አካባቢ ጦር መሳሪያ ማከማቸትና የጦር ልምምድ ማድረግ፥ የስለላ፥ የሃሰት መረጃ የመናኘት ተግባር)።

ቅዝቃዜ ስ ብርድ።

ተቀዛቀዘ ግ የብርድ ስሜት ተሰማ።

ማቀዝቀዣ ስ ምግብን፥ መጠጥን፥ መድሃኒትንና የመሳሰለውን ነገር ለተወሰነ ጊዜ ሳይበላሽ አቀዝቅዞ የሚያቆይና ፈሳሽ ነገርን ወደ በረዶነት ሊለውጥ የሚችል፥ በሳጥን ወይም በቁምሳጥን ቅርፅ የተሰራ የቤት እቃ፡ ፍሪጅ፥ በረዶ ቤት።

ቀዘባ ስ 1. ፍሬ ሊይዝ የተቃረበ የስንዴ፥ የገብስ ፥...ቡቃያ፥ ሰብል። 2.(ዘይ.) ዛላው፥ ቁመናው ያማረ፡ የተዋበ፡ ለግላጋ፡ ሰታ።

ቀዘነ ግ 1. ቀጭን አይነምድር ተቀመጠ፡ ኮሳ፡ ተፀዳዳ። 2. (ዘይ.) ፈራ፡ ሰጋ፡ ተርበደበደ።

ቅዘን ስ ቀጭን አይነ ምድር፡ ተቅማጥ።

ቅዘን በቅዘን ሆነ በጣም ፈራ፥ ተርበደበደ።

ቅዘን ነዳው "ተቅማጥ ነዳው" ን ተመ.

ቅዘናም ቅ (ስድብ) ፈሪ፡ ጸርጻሪ፡ ሃሞተ ቢስ፥ ቦቅቧቃ።

ቀዘዘ ግ ፈዘዘ።

ቀዛዛ ቅ ፈዛዛ፥ የቀዘዘ።

ቅዝዝ አለው ፈዘዘ፡ ቀፈፈው።

ቀዘፈ ግ በውሃ ላይ በታንኳ፥ በጀልባ፥...ለመሄድ ወይም ለመዋኘት እንዲያስችለው በመቅዘፊያ ወይም በእጅ ውሃውን ወደ ኋላው ግራና ቀኝ ገፋ።

መቅዘፊያ ስ ታንኳን፥ ጀልባን፥... በውሃ ላይ ለመቅዘፍ፥ ለመምራትና ውሃውን በመግፋት በሚገኝ ተቃራኒ ሃይል ታንኳው ወይም ጀልባው ወደፊት እንዲሄድ ለማድረግ የሚረዳ፡ ከጫፉ ጠፍጣፋ ያለ እቃ፤ ትርክዛ።

ቀዛዛ "ቀዘዘ" ስር ተመ.

ቀዝቃዛ "ቀዘቀዘ" ስር ተመ.

***ቀዠቀዠ**

ቀዥቃዣ (ቀዠቀዥ) ቅ (ስድብ) ከውካዋ፡ አንድ ቦታ ረግቶ የማይቆይ፥ ከለፍላፋ።

ቀዥቀዥ አለ ግ ተንቀዠቀዠ።

ቅዥቅዥ አለ ግ በጣም ተንቀዠቀዠ።

ተንቀዠቀዠ ግ ተንከወከወ፥ ተክለፈለፈ፥ ተቅለበለበ።

አንቀዠቀዠ ግ አንከወከወ፥ አክለፈለፈ፥ አቅለበለበ።

***ቀየመ(ቄመ)**

ቂም ስ በደል የተፈፀመበት ሰው፡ በተፈፀመበት በደል ምክንያት የሚይዘው የቁጭት፥ የጥላቻ ስሜት፡ ቁርሾ።

ቂሙን ቀረፈ ቂሙን ተወ።

ቂሙን ተወጣ ተበቀለ፥ የበቀል እርምጃ ወሰደ።

ቂም አበቀለ ተቀያየመ፥ ተቃቃረ።

ቂም ያዘ 1. አቄመ፡ በተደረገበት በደል ምክንያት የቁጭት፥ የጥላቻ፥ የበቀል ስሜት አደረበት። 2. ቶሎ አልድን አለ፥ አቀበረ፥ አመረቀዘ (ቁስል)።

ቂም በቀል ስ 1.ቂምን ለመወጣት የሚወሰድ ወይም የተወሰደ ርምጃ። 2. በቂም ላይ የተመሰረተ ጥላቻ፥ ክፉ ሃሳብ።

ቂመኛ ቅ 1.ቂም የሚይዝ፡ የተፈፀመበትን በደል የማይረሳ። 2. ቂም የያዘ፡ የተፈፀመበትን በደል ያልረሳ ጠበኛ፡ ደመኛ። *እኔና እሱ ቂመኞች ነን።*

ቅያሜ ስ በፀብ፡ በጥል፡ ባለመስማማት ምክንያት የሚፈጠር ቅሬታ፥ የጥላቻ ስሜት።

ቅይም አለ ግ 1. ክፋት አለው ተቀየመ። 2. በድንገት ከፊቱ ላይ የመቀየም፥ ቅር የመሰኘት ስሜት አሳየ። 3. ጠላ፥ ተጠየፈ።

ተቀየመ ግ በደረሰበት ወይም በተፈፀመበት በደል ምክንያት ተከፋ፡ ጥላቻ፥ ቅሬታ አደረበት፡ አኮረፈ።

ተቀያየመ ግ እርስ በርስ አንዱ በሌላው ቅር ተሰኘ፥ ተኮራረፈ።

አቄመ ግ 1. በተደረገበት በደል ምክንያት የቁጭት፥ የጥላቻ፥ የመበቀል ስሜት አደረበት። 2. ቶሎ አልድን አለ፥ አቀበረ፥ አመረቀዘ (ቁስል)።

አቀያየመ ግ አጣላ፥ አኮራረፈ።

አቀያያሚ ቅ ከሌላው ጋር የሚያጣላ፡ የሚያጋጭ (ነገር፥ ጉዳይ)።

አስቀየመ ግ 1. ቅር አሰኘ፡ አስከፋ፡ እንዲቀየም አደረገ። 2. መጥፎ ሆነ፥ አስጠላ፥ አስጠየፈ (መልኩ፡ ስራው፥...)።

አስቀያሚ ቅ (ስድብ) አስጠሊታ፥ መጥፎ፥ አስከፊ፥ አስጠያፊ (መልክ፡ ስራ፡...)።

ቀየረ ግ 1. ለወጠ፡ ሌላ አደረገ። 2. ተካ። *ዘበኛውን የሚቀይረው ሰው አልተገኘም*። 3. ተለወጠ፡ ሌላ ሆነ (መልኩ፥ ቀለሙ፥...)። 4. ተበላሸ፥ ለወጠ (ጣእሙ፡ ሽታው፡...)። 5. አዛወረ፥ ከነበረበት ቦታ ለወጠ።

መቀየሪያ ስ መለወጫ፡ ቅያሪ፥ (በትርፍነት ያለ)።

ቅያሪ (ቅያሬ) ስ 1. ዝውውር (የስራ ቦታ)።

2. በአንድ ነገር ምትክ የሚሰጥ፥ የሚወሰድ ወይም የሚያገለግል መለወጫ።

ቅይር አለ ግ በጣም ተቀየረ፡ ተለወጠ፡ ፊት ከነበረበት ሁኔታ ተለየ።

ቀያየረ ግ አንዱን በሌላ ተካ፥ ለዋወጠ።

ተቀየረ ግ 1. ተለወጠ፥ ሌላ ሆነ። 2. ፊት ከነበረበት ሁኔታ፥ መልክ፥ ጠባይ፥... የተለየ ሆነ። 3. ተዛወረ፥ ለወጠ (ለስራ፥...)።

ተቀያሪ ቅ 1. ተተኪ፡ ተለዋጭ፡ ምትክ። 2. ሊለወጥ፡ በሌላ ሊተካ የሚችል።

ተቀያየረ ግ 1. እርስ በርስ አንዱ የሌላውን ወሰደ፥ ተለዋወጠ። 2. ፊት ከነበረበት ሁኔታ፡ መልክ፥ ጠባይ፥... የተለየ ሆነ። 3. ተተካካ፡ ተለዋወጠ።

ተቀያያሪ ቅ ተለዋዋጭ፡ የሚቀያየር።

ቀየሰ ግ የቦታን ርቀት፥ ስፋት፥ ከፍታ፥ አቅጣጫ በሚትር፥ በገመድ፡ በልዩ ልዩ መሳሪያ ለካ፥ ሰፈረ፥ መጠነ፥ ገመገመ።

ቀያሽ ስ የቅየሳ ስራ ባለሙያ።

ቅየሳ ስ የተወሰነ የቦታን ርቀት፥ ስፋት፥... በተለያዩ ዘመናዊ መሳሪያዎች የመለካት ጥበብ፥ ዘዴ፥ ትምህርት።

ቅያስ ስ ልክ፥ መጠን፥ ንድፍ (የቦታ፥ የመንገድ፥ የቤት፥...)።

ተቀየሰ ግ ተለካ፥ ተመተረ (መንገድ፥ ቤት ለመስራት)።

ቀየደ ግ 1. አሰረ፥ ጠፈረ፥ ሰነከለ(የከብት እግርን)። 2. ኮልታፋ፥ ለንባዳ አደረገ፤ መናገር ከለከለ (አንደበትን)።

መቀየጃ ስ ማሰሪያ ገመድ፥ ጠፍር።

ቅይድ ቅ የታሰረ፥ የተሰነከለ።

ቀየጠ ግ ቀላቀለ፡ ደባለቀ።

ቅይጥ ቅ 1.ቅልቅል፥ ድብልቅ። ስ 2. የተለያዩ እህሎችን በመደባለቅ የተዘጋጀ እንጀራ።

ቅይጥ አለ ግ ተቀየጠ።

ተቀየጠ ግ ተቀላቀለ፥ ተደበላለቀ።

አቀያየጠ ግ አቀላቀለ፥ አደበላለቀ።

ቀያሽ "**ቀየሰ**" ስር ተመ.

ቀያቂ "**ቀሳ**" ስር ተመ.

ቀያየረ "**ቀየረ**" ስር ተመ.

ቀይ "**ቀላ**" ስር ተመ.

ቀደመ ግ 1. አለፈ፥ ከፊት ሆነ (በሩጫ፡ በእካሄድ፥...)። 2. መጀመሪያ ሆነ። *ለእንጀራው ወጡ ቀደመ*። 3. ሊሳው ከማድረጉ በፊት እሱ አደረገ፤ ሰራ። 4. (ዘይ.) ከመመታቱ በፊት አስቀድሞ እሱ መታ (በጥል ሳይ)።

በቀደም ተው.ግ. አሁን ለታ፥ በቅርብ፥ ካለፉት ቀናት ውስጥ በአንዱ።

ቀድሞ ተው.ግ ድሮ፥ ጥንት፥ ፊት።

ቀድሞውኑ ፊቱኑ፥ መጀመሪያውኑ። *ቀድሞውኑ ተናገሬ ነበር*።

መቅድም ስ በመፅሃፍ የመጀመሪያ ገፆች ላይ የሚፃፍ፥ አብዛኛውን ጊዜ ስለመፅሃፉ አጠቃላይ መግለጫ የሚሰጥ ፅሁፍ።

ቀደምት ቅ የቀደሙት፥ የድሮዎቹ፥ የጥንቶቹ፥ የመጀመሪያዎቹ።

ቀዳሚ ቅ 1. ፊት መሪ። 2. የቀደመ። 3.ጀማሪ።

ቀዳማ^{1} ስ 1.የመጀመሪያ እርሻ፥ ጭፍለቃ፥ እዳሪ ማውጣት። 2.የኮርቻ የፊተኛ ድጋፍ። ቀዳማይ እየተባለም ይጠራል(ስእሉን ኮርቻ ስር ተመ.)።

ቀዳማዊ ቅ አንደኛ፥ የመጀመሪያ።

ቅደም ተከተል ስ ተራ፥ ቀዳሚና ተከታይ።

ቅድመ አያት ስ የአያት እናት ወይም አባት፥ ሁለተኛው አያት።

ቅድሚያ ስ ከሁሉም በፊት የመሆን፥ የመገኘት፥ የማግኘት እድል፡ መብት።

ቅድሚያ ክፍያ ስ አንድን እቃ ለመግዛት ወይም አንድን አገልግሎት ለማግኘት አስቀድሞ የሚከፈል ሙሉ ወይም የተወሰነ ክፍያ።

በቅድሚያ ተው.ግ. በመጀመሪያ።

ቅድም ስ ከጥቂት ደቂቃዎች ወይም ሰአታት በፊት ያለው ጊዜ።

ቀደም ቀደም አለ ቶሎ ቶሎ አለ፥ ጠደፍ ጠደፍ አለ፤ ተንቀሳቀሰ።

ቀደም ብሎ ተው.ግ. አስቀድሞ፡ በፊት።

ተቀደመ ግ 1. ታለፈ፡ ወደሂላ ሆነ። 2. (ዘይ.) ሳይመታ ተመታ። 3. እሱ ከማድረጉ በፊት ሌላ ወገን ፈጥኖ አደረገ ወይም ሰራ።

ተቀዳሚ ቅ ቀዳሚ፥ በኩር፡ የመጀመሪያ።

ተቀዳደመ ግ ተሳሰፈ፡ ፊትና ሂላ ሆነ።

ተሽቀዳደመ ግ 1. በሩጫ፥ በግልቢያ፥... አንዱ ሌላውን ለመቅደም ተወዳደረ፥ ተፎካከረ። 2. ቸኮለ፡ ፈጠነ፥ ቀደመ። *ሳይሆንም አያልኩት ተሽቀዳድሞ ሂሳቡን እሱ ከፈለ*።

አቀዳደመ ግ አስተላለፈ፡ ፊትና ሂላ አደረገ።

አስቀደመ ግ አሳለፈ፥ ፊት አደረገ፥ ቅድሚያ ሰጠ።

አስቀድመኝ መጀመሪያ እኔን ግደለኝ (ከምወዳቸው በፊት)።

አስቀድሞ ተው.ግ. መጀመሪያ፡ ቀደም ብሎ፡ ከሁሉ በፊት።

አሸቀዳደመ ግ በሩጫ፣ በግልቢያ፣... አወዳደረ፥ አፎካከረ።

እሽቅድድም (**እሽቅድምድም**) ስ የሩጫ፥ የግልቢያ፣... ውድድር፣ ፉክክር።

ቀደሰ ግ 1. ስርአተ ቅዳሴን ለማካሄድ በተዘጋጀው ስጋወደሙ ላይ ተገቢውን ፀሎትና ምስጋና በማቅረብ ራሱም ቆርቦ ምእመናንን አቆረበ። 2. አነፃ፥ አጠራ፥ ባረከ። 3. ጀመረ።

ቀዳሽ ስ የቅዳሴ ስነ ስርአት የሚያከናውን ቄስ ወይም ዲያቆን።

መቅደስ ስ በቤተክርስቲያን ውስጥ ስልጣነ ክህነት ያላቸው ካህናት ብቻ የሚገቡበት፣ ታቦቱና መንበሩ የሚገኙበትና ቅዳሴ የሚቀደስበት ክፍል።

ቅዱስ (ብ.ቁ.**ቅዱሳን**፤ አን.**ቅድስት**፤ አን. ብ.ቁ. **ቅዱሳት**) ቅ 1. የተቀደሰ፥ የተባረከ፥ የነፃ፥ የበቃ፥ ንፁህ፣ ብሩክ። 2. ጠባየ መልካም። 3. ርኩስ ያልሆነ።

ቅዳሴ ስ ስልጣነ ክህነት ባላቸው ቀሳውስት፥ ዲያቆናት፣...አማካይነት በስጋወደሙ ላይ በዜማና በንባብ የሚፀለይ ፀሎት፣ ፀሎቱ የተፃፈበት መፅሃፍም ቅዳሴ ይባላል።

ቅዳሴ ወጣ ቅዳሴውን ፈፀመ፥ አበቃ።

ቅዳሴ ገባ ቅዳሴ ጀመረ።

ቅዳሴ ገባ የቅዳሴውን ስነስርአት ከሚያከናውኑት አንዱ በመሆን ወደ መቅደስ ገባ።

ቅዳሴ ጠበል ስ ከቅዳሴ ስነስርአት በኋላ ምእመናን በፀበል መልክ የሚቀምሱት የተቀደሰበት ውሃ።

ቅድስና ስ ቅዱስነት፥ ንፅህና፥ ብሩክነት።

የተቀደሰ ቅ የተከበረ፥ የተባረከ።

አስቀደሰ ግ የቅዳሴ ስነስርአት በሚካሄድበት ቦታ ተገኝቶ የፀሎቱ ተካፋይ ሆነ።

አስቀዳሽ ስ በቅዳሴ ስነስርአት ላይ ተገኝቶ የፀሎቱ ተካፋይ የሚሆን ምእመን።

ቀደደ ግ 1. ሰነጠቀ፣ ተለተለ፣ ሸረከተ (ጨርቅን፣ ወረቀትን)። 2. በሳ፥ ሸነቆረ፥ ነደለ። 3. ከፈተ፥ ጀመረ።

ቀዳዳ ቅ 1. የተሰነጠቀ፣ የተሸረከተ። *ከቀዳዳ ይሾላል ወምዳዳ*፡2. ብስ፥ ሽንቁር። 3.(ዘይ.፣ ሲድብ) ምስጢር፥ ነገር የማይቋጥር፣ ወሬኛ (ሰው)።

ቀዶ ህክምና ስ በአደጋ ወይም በበሽታ ምክንያት የተጎዳን አካል በመቅደድና በመስፋት ህክምና የመስጠት ዘዴ፤ ኦፕራሲዮን።

ቅዳጅ ስ ከጨርቅ፥ ከወረቀት፥... ተቀዶ የወጣ ብጫቂ፥ ብጣቂ፥ እራፊ፥ ቁራጭ።

ቅድ ስ 1. የልብስ ስፌት የአቀዳደድ አይነት። *ሾንጉላ ቅድ ቀሚስ*፡ 2. (ዘይ.) ምስጢር የማይቋጥር፥ ወሬኛ።

ተቀደደ ግ 1. ተሸረከተ። 2. (ዘይ.) ዋሸ፣ ውሸት ነገር አወራ።

ተቀዳጅ ቅ በቀላሉ ሊቀደድ፥ ሊሸረከት የሚችል።

ተቀዳደደ ግ በእርጅና ወይም በሌላ ምክንያት ተበጫጨቀ፥ ተሸረካከተ።

አስቀደደ ግ ልብስ ለማሰፋት በልኩ አስቆረጠ፥ በልኩ እንዲሰፋለት አደረገ።

ቀዳ ግ 1. ፈሳሽ ነገርን፥ ለምሳሌ ውሃን ከወንዝ ወይም ፈሳሹ ከአለበት ቦታ በእቃ አድርጎ በተወሰነ መጠን ጨለፈ፥ ወሰደ። 2.አንቆረቆረ፥ ጨመረ፥ ሰጠ። *ለባላሬው ሁለት ብርሌ ጠጅ ቀዳለት*። 3. አመጣ። *ውሃ ከቀዳች በኋላ ወደ ገበያ ሄደች*። 4. ገለበጠ (ፅሁፍን ወይም ሌላን ነገር ከሌላው ላይ)። 5. ቀረፀ (ድምፅን)። 6. ኮረጀ።

ቀዳው በብዛት አወረደው፥ አዥጎደጎደው። *ዝናቡን ቀዳው/ወሬውን፥...* ቀዳው።

መቅጃ ስ 1. መጥለቂያ፥ መጭለፊያ፤ ፈሳሽ ነገር ከአንዱ ወደሌላው የሚገለበጥበት ወይም የሚወሰድበት እቃ። 2. ውሃ የሚቀዳበት ስፍራ፥ ምንጭ፣ ኩሬ፥ ወንዝ፥...። 3. በቴፕ፥ በሸክላ፥... የሚቀረፀውን ድምፅ መቀበያ፥ ማስተላለፊያ መሳሪያ።

ቅድ ስ ከአንድ መፅሃፍ ተውጣጥቶ በከፊል የተፃፈ ፅሁፍ። *ቅድ ድጓ*።

ቅጂ ስ 1. ጠላ ተጠምቆ፣ ጠጅ ተጥሎ፥ ቅቤ ተነጥሮ፥... የሚገኘው ውጤት፣ የተጣራው ክፍል። *አንድ ጋን ጠላ አራት እንስራ ቅጂ ይወጣዋል*። 2. ከሌላ የተገለበጠ፣ የተወሰደ ፅሁፍ ወይም የተቀረፀ ድምፅ። 3. የመጀመሪያውን መስሎ የተሰራ፥ የተገለበጠ፥ የተቀረፀ (ፅሁፍ፣ ደብዳቤ፣...)፤ ኮፒ።

ተቀዳው 1. ወጣው። *ጋኑ አራት እንስራ ጠጅ ተቀዳው*። 2. ብዙ ፈሰሰው። *እንባ ተቀዳው*።

ቀዳሚ "**ቀደመ**" ስር ተመ.

ቀዳማ ዝ.ክ.

ቀዳማዊ ዝ.ክ.

ቀዳማይ "**ቀደመ**" ስር የ"**ቀዳማ**"ን 2ኛ ፍቺ ተመ.

ቀዳሚት "**ቅዳሜ**"ን ተመ.

ቀዳሽ "**ቀደሰ**" ስር ተመ.

ቀዳዳ "**ቀደደ**" ስር ተመ.

***ቀዳጀ**

ተቀዳጀ ግ አገኘ፣ ተጎናፀፈ (ድልን፣ ክብርን፣ ዘውድን)።

አቀዳጀ ግ ሰጠ፤ አስገኘ፥ አጎናፀፈ (ድልን፥ ክብርን፥...)::

ቀጋ ስ እንጨቱና ፍሬው የፅጌረዳ ተክል የሚመስል፥ እሾህ ያለው የእፅዋት አይነት:: ፍሬውም ቀጋ ይባላል::

ቀጠለ ግ 1. ተቋርጦ የነበረውን ስራ፥ ድርጊት፥... እንደገና ጀመረ፥ ማካሄድ ያዘ፥ ገፋ:: 2. ተቋርጦ የነበረው ስራ፥ ድርጊት፥... እንደገና ተጀመረ:: 3. የጀመረውን ስራ ፥ ድርጊት፥... ሳያቋርጥ አካሄደ፥ በዚያው ገፋ:: 4. የተጀመረው ስራ፥ ድርጊት፥... ሳይቋረጥ ተካሄደ፥ በዚያው ገፋ:: 5. ጨመረ፥ አከለ፥ ከፍ አደረገ (ቁመትን፥ ርዝማኔን) :: 6. ከፍ አለ፥ ጨመረ፥ በዛ:: *የልጅቷ ቁመት ቀጠለ::* 7. አያያዘ፥ አገናኘ፥ ቋጠረ (የተበጠሰን፥ ለየብቻ የነበረን፥ የተለያየን ነገር):: 8. ተከተለ፥ ለጠቀ፥ ተራ ያዘ:: *ከዚህ ቀጥሎ ሌላ ይመጣል::* 9. አገባ፥ መስመር ዘረጋ(የውሃ፥ የኤሌክትሪክ፥...)::

ቀጥል ሂድ፥ አድርግ፥ ጀምር::

ቀጠባ ስ 1. ከወለላ በቀር ክዳና ቀለህ የሌለበት የማር እንጀራ:: 2. በግንብና በካብ ቅጥር ላይ የተቀመጠ የድንጋይ ክዳን፥ ድምድማት:: 3. "ቀፀባ" ን ተመ.

ቅጥል (ቅፅል) ቅ 1. የተቀጠለ:: 2. "ቅፅል"ን በፊደል ተራው ተመ.

ቅጥይ (ቅጥያ) ስ 1. ቅርንጫፍ፥ አፅቅ:: 2. በሌላ ነገር ላይ የተቀጠለ፥ የተጨመረ፥ የታከለ፤ ዋና ያልሆነ::

ቀጣጠለ ግ 1. የተለያየውን ወይም የተበጣጠሰውን እርስ በርሱ አያያዘ፥ ቋጠረ:: 2. ጨማመረ፥ አከለ (ወሬን)::

ቅጥልጥል ቅ የተያያዘ፥ ያልተቋረጠ:: *ቅጥልጥል ጽሑፍ / ቅጥልጥል ቤት::*

ተቀጣይ ቅ ተጨማሪ ሆኖ የተያያዘ ወይም የሚያያዝ::

ተቀጥላ (ተቀፅላ) ስ 1. ተጨማሪ፥ ተደራቢ፥ ትርፍ ነገር:: 2. በሌላ ዛፍ ላይ ጥገኛ ሆኖ ወይም ተጣብቆ የሚበቅል የእፅዋት አይነት::

ተቀጣጠለ ግ አንዱ ከሌላው ጋር ተያያዘ፤ ያልተቋረጠ ወይም ቅጥልጥል ሆነ::

አቀጣጠለ ግ አንዱን ከሌላው ጋር አያያዘ፥ ቀጣጠለ::

ቀጠረ^1 ግ በየተወሰነ ጊዜ በሚሰጥ ክፍያ ወይም ደሞዝ ስራ ለማሰራት ከሰራተኛ ጋር ተዋዋለ፤ ሰራተኛ ወሰደ፥ አስገባ::

ቀጣሪ ስ አሰሪ (ግለሰብ፥ ድርጅት፥...)::

ቀጣሪና አስቀጣሪ ስ አሰሪና ሰራተኛን የሚያገናኝ አዋዋይ፤ ደላላ::

ቅጥር ስ 1. የተቀጠረ፤ ለግለሰብ፥ ለድርጅት ፥...በክፍያ ወይም በደመወዝ የሚሰራ:: 2. አቀጣጠር፤ የአቀጣጠሩ ሁኔታ፥ ክንዋኔ:: *ቅጥሩ የሚከናወነው በምናው መ/ቤት በኩል ነው::*

ቅጥረኛ ስ አንድ ነገር እንዲፈፅም፥ እንዲሰራ በክፍያ ወይም በጥቅም የተገዛ (ብዙውን ጊዜ ለወንጀል ስራ):: *በቅጥረኛ ተገደለ::*

ተቀጣሪ ቅ በገንዘብ ወይም በሌላ ጥቅም ተዋውሎ ለግለሰብ፤ ለድርጅት፥... የሚሰራ፥ ግልጋሎት የሚሰጥ::

ቀጠረ^2 ግ ቦታና ጊዜ ወስኖ ነገረ (አንድ ነገር ለማድረግ፤ ለመገናኘት፥...)::

ቀጠሮ ስ አንድ ነገር ለመስራት፥ ለመገናኘት፥... የሚደረግ የቦታ፥ የጊዜ ውሳኔ:: *የትና መቼ እንደምንገናኝ ቀጠሮ እናድርግ::* 2. ባለጉዳዮች የተስማሙበትና የወሰኑት የመገናኛ ቦታና ጊዜ:: *ቀጠሮህ የትና መቼ ነው?*

ቀጠሮ ሰጠ ጊዜና ቦታ ወስኖ ነገረ፥ ቀጠረ (ለመገናኘት፥ አንድ ነገር ለማድረግ)::

ቀጠሮ ተቀበለ የትና መቼ መገኘት እንዳለበት አወቀ፥ የቀጠሮው ጊዜና ቦታ ተወስኖ ሲነገረው ተስማማ::

ቀጠሮ አከበረ በቀጠሮው ሰአት በቦታው ተገኘ::

ቀጠሮ አክባሪ ቅ በተቀጠረበት ወይም በተቃጠረበት ቦታ በጊዜው የሚገኝ::

ቀጠሮ አፈረሰ በቀጠሮው ሰአት በቦታው ሳይገኝ ቀረ::

ቀጠሮ አፍራሽ ቅ በቀጠሮው የማይገኝ::

ቀጠሮ ያዘ የሚገናኝበትን ቦታና ጊዜ ወሰነ፥ አስወሰነ::

ቀጠሮ ጠየቀ ቀጠሮ እንዲሰጠው አመለከተ፥ አሳሰበ::

ተቀጣጠረ (ተቃጠረ) ግ አንድ ነገር ለማድረግ ወይም ለመገናኘት ቦታና ጊዜውን በመወሰን ተስማማ::

መቃጠሪያ ስ ቀጠሮ የሚደረግበት መገናኛ ቦታ::

አቃጠረ ግ 1. ወንድና ሴትን ለወሲብ ወይም ለፍቅር ስራ አገናኘ፤ አስማማ:: 2. አሳበቀ፤ ወሬ አቀበለ::

አቃጣሪ ስ (ስድብ) 1.ወንድና ሴትን ለፍቅር ስራ የሚያገናኝ::2. አሳባቂ፥ ወሬ አቀባይ::

አስቀጠረ ግ ጉዳዩ የሚታይበትን ቀን አስወሰነ::

ቀጠረ^3 ግ አጠረ፤ ከበበ፤ ከለለ::

ቅጥር(ቅፅር) ስ አጥር::

ቅጥር ግቢ (ቅፅረ ግቢ) ስ በአጥር የተከለለ ግቢ፥ የተከበበ ቦታ::

ቀጠሮ "ቀጠረ^{2}" ስር ተመ.

ቀጠቀጠ ግ 1. አንድን ነገር ለመስበር፤ ለማዝለጥ፤ ለማቅናት፤ ለመጠፍጠፍ፤... በመዶሻ ወይም በሌላ መሳሪያ ደጋግሞ መታ። 2.ወቀጠ፡ አደቀቀ፤ ሰባበረ። 3. ደጋግሞ መታ፡ ደበደበ፤ ጨፈጨፈ። *ሰውየውን እንደእባብ ቀጠቀጠው።* 4. መታ፤ ጉዳት አደረሰ። *መዶሻው ጣቴን ቀጠቀጠው።* 5. አኮላሸ፡ ወቀጠ (የወይፈንን፡ የበግን፡ የዘር ማመንጫ)። 6. አንኳኳ፤ ደጋግሞ በሃይል መታ (በርን፡ ግርግዳን፤...)። 7. ጎዳ፤ አሰቃየ። *በሽታ ቀጠቀጠው።*

ቀጥቅጦ ገዛ ጨቁኖ፡ ረግጦ ገዛ።

ቀጥቃጭ ስ (የን.አነ.) ብረትን በማቅለጥና በመቀጥቀጥ የተለያዩ ነገሮችን የሚሰራ የእደጥበብ ባለሙያ።

ቅጥቃጤ ስ የሌሊት ቅገርት።

ቅጥቅጥ ስ 1. ለመብራትነት የሚያገለግል የተቀጠቀጠ እንጨት። ቅ 2. የተኮላሸ፤ የተወቀጠ (በሬ፡ ፍየልና በግ)። 3. በመደብደብ፡ በመመታት ወይም በሌላ አደጋ ምክንያት የህመም ስሜት ያለበት አካል ወይም ገላ።

እንቅጥቃጭ (ቅጥቃጭ) ስ ገብስና ስንዴን የመሳሰለ እህል፡ ተወቅጦ ወይም ተከክቶ ሲበጠር ወይም ሲንቀረቀብ ተለይቶ የሚወጣው ትንንሹና ስብርባሪው ክፍል።

***ቀጠቀጠ**

ቀጥቃጣ(ቀጠቀጥ) ቅ 1. በህመም ወይም በሌላ ምክንያት አካሉ የሚንቀጠቀጥ፡ የሚንዘፈዘፍ። 2. ስስታም፤ ገብጋባ፡ ንፉግ፡ ቆጥቋጣ። 3. ፈሪ፤ ቡከን።

ተንቀጠቀጠ ግ 1. በፍርሃት፤ በብርድ፤ በበሽታ፡... አካሉ ራደ፤ ተንዘፈዘፈ፤ ተርገፈገፈ። 2. ሰሰተ፤ ተንገበገበ።

አንቀጠቀጠ ግ 1. አራደ፤ አንዘፈዘፈ፤ አርገፈገፈ (ፍርሃት፤ ብርድ፤ በሽታ)። 2.አሰሰተ፤ አስገበገበ። *ላንድ ብር ለመስጠት ምን ያንቀጠቀጠህ።*

አንቀጥቅጦ ገዛ ሰው ለጥ እንዲል አድርጎ፤ አስጨንቆ ገዛ።*የአውራጃውን ህዝብ አንቀጥቅጠው ይገዙት ነበር።*

ቀጠበ ግ 1. ለካ፤ መጠነ፤ ምልክት አደረገ (ሸማኔ ድርን)። 2. ወሰነ፡ መጠነ (ለምሳሌ እድሜን፤...)።

መቀጠቢያ ስ በክንድ የተመጠነ የሸማኔ መለኪያ፡ ድሩ ላይ ምልክት ማድረጊያ እንጨት፤ ዘንግ።

ቅጥብ ስ 1. እየተሰራ ባለ የሸማ ድር ላይ በመቀጠቢያ ተለክቶ፡ ተመጥኖ የተደረገ ምልክት። 2. የእድሜ መጨረሻ፤ ወሰን። *ቅጥቡ ሲሞላ ሞተ።*

ቅጥባት ዝ.ከ.

ቅጥጥብ ስ ዝብዝት፡ ሽሙጥ።

ተቀጣጠበ ግ ተዘባበተ፡ አፌዘ፤ አሽሟጠጠ።

ቀጠነ ግ 1. አነሰ፡ ሳሳ፡ ቀነሰ፡ ሰለለ (አካል)። 2. ውፍረት፡ ልድላዴ አጣ፡ ወደ ውሃነት ተጠጋ (ፈሳሽ ነገር)።

ቀጭን (ቀጪን)(ብ.ቁ.ቀጫጭን) ቅ 1. ውፍረት የሌለው፡ የሳሳ፡ የሰለለ (አካል)። 2. ውፍረት፡ ልድላዴ የሌለውና ወደ ውሃነት የተጠጋ (ፈሳሽ)። 3. ለቁመቱ ተመጣጣኝ የሆነ በቂ ውፍረት የሌለው (ሰው)።

ቀጭን እመቤት ራሷን የቻለች ሃብታም ሴት።

ቀጭን ጌታ ራሱን የቻለ ሃብታም ሰው።

ቀጭን ሰጥር ስ 1.ከጎድን ሁሉ የምትቀጥን ቀጭን የጎን አጥንት። 2. እንደውጋት አድርጎ የሚያም የወገብ ላይ በሽታ።

ቀጭን ድምፅ ስ ጎርናና ያልሆነ ወይም እንደፉጨት ያለ ድምፅ።

ቀጭን ፈታይ ቅ በፈትል ስራ ባለሙያ የሆነች፤ በቀጭኑ የመፍተል ችሎታ ያላት (ሴት)።

ቀጠና ስ የረሃብ ዘመን፡ ችጋር።

ቀጠጠ^{1} ግ 1.እንዳይበላሸ አድርጎና አስተካክሎ ሸለተ፤ አጨደ፤ ቆረጠ፡ ቁመቱን አሳጠረ (ለጠጉር፡ ለሳር፤...)።2. ጉብጠትን፤ ጠማማነትን እያነፀ፤ እየቀረፀ አስተካከለ፡ አሳመረ።

ቀጠጠ^{2} ግ ነፋ፡ ቀበተተ፤ አሳበጠ (ሆድን)።

ተቀጠጠ ግ ተነፋ፡ ተቀበተተ፤ አበጠ።

ቀጠጥና ስ ቅርፃቸው የአህያ ጆሮ የሚመስል ሾካራና አመድማ የሆኑ ሰፋፊ ቅጠሎች ያሉት የእፅዋት አይነት፤ የአህያ ጆሮም ይባላል።

ቀጠጦ ስ የማሽላ አይነት።

ቀጠፈ^{1} ግ 1. ቆረጠ፡ በጠሰ፡ ቀነጠበ (የዛፍ፤ የተክል ቅጠልን፤...)። 2. (ዘይ.)ቀሰፈ፡ ያለጊዜው ገደለ፤ ቀጨ።

ተቀጠፈ ግ 1. ተበጠሰ፡ ተቆረጠ፡ ተቀነጠበ። 2.(ዘይ.) ተቀጨ፤ ተቀሰፈ፤ ያለጊዜው ሞተ።

ቀጠፈ^{2} ግ አበለ፡ ዋሸ።

ቀጣፊ ቅ ዋሾ፤ አባይ፤ አጭበርባሪ።

ቅጥፈት ስ ውሸት፤ አብለት፤ ሃሰተኛ ቃል።

ቀጣጠፈ ግ አበለ፡ ዋሸ፤ የሆነ ያልሆነውን ተናገረ።

ቅጥፍጥፍ አለ ግ ዋሸ፤ ወሻከተ።

ቀጣ ግ 1. ላደረገው ጥፋት ወይም ላደረሰው በደል አጥፊውን ገንዘብ አስከፈለ፡ አሰረ፤ መታ፤...። 2. አሰቃየ፡ አጎሳቆለ። *በላለማችን*

ላይ ረሃብ የቀጣው ህዝብ ቁጥር ቀላል አይደለም። 3. ከጥፋት እንዲታረምና በስነስርአት እንዲያድግ ገሰፀ፡ ተቆጣጠረ፤ ቀነበጠ (አሳዳጊ ልጅን፤ ታላቅ ታናሽን)። 4. (ስፖ.) ዳኛ አጥፊ ቡድንን ወይም ተጫዋቾችን ለተወሰነ ጊዜ ከጨዋታ (ከውድድር) አገደ፡ አስወጣ ወይም ሌላ ውሳኔ ሰጠ።

መቅጫ ስ መገረፊያ፤ መደብደቢያ (አለንጋ፡ አርጩሜ፡...)።

ቅጣት ስ ጥፋት በፈፀመ ግለሰብ፤ ቡድን ወይም ድርጅት ላይ የሚሰጥ ውሳኔ (የእስር፡ የገንዘብ ክፍያ፡...)።

[የ]ቅጣት ምት ስ (ስፖ.) ከፍፁም ቅጣት ክልል ውጭ፤ ከሁለት ቡድኖች የአንደኛው ቡድን ተጫዋች ጥፋት ሲፈፅም (ለምሳሌ ኳስን በእጅ በመንካት፤ በመጋፋት፤ በመጥለፍ፡ አንድን ተጫዋች ለሁለት በመያዝ፤... የመሳሰሉ ጥፋቶች ሲፈፀሙ) ለተቃራኒው ቡድን የሚሰጥ ምት።

ቅጣተኛ ቅ ቅጣት የተቀበለ ወይም የተበየነበት።

ተቀጣ ግ 1. ላደረገው ጥፋት ወይም ለፈፀመው በደል ገንዘብ ከፈለ፡ ታሰረ፡ ተመታ፤ ተገደለ ወይም ሌላ አይነት ጉዳት ደረሰበት። 2. ተሰቃየ፤ ተጎሳቆለ። *ህዝቡ በረሃብ ተቀጣ፡* 3.(ስፖ.) አጥፊው ቡድን ወይም ተጫዋቹ ለተወሰነ ጊዜ ከጨዋታ (ከውድድር) ታገደ፤ ወጣ ወይም ሌላ ውሳኔ ተወሰነበት። 4.(ዘይ.) ተሸነፈ፡ ድል ሆነ። 5. ከጥፋት እንዲታረምና በስነስርአት እንዲያድግ በየጊዜው ምክር፡ ተግሳፅ ወይም ሌላ ቅጣት ተሰጠው። *ተቀጥቶ ያደገ ልጅ ነው።* 6. ቀደም ሲል በደረሰበት ቅጣት ወይም ችግር ምክንያት ጥፋቱን እንዳይደግም ትምህርት ወሰደ።

መቀጫ(መቀጮ) ስ ጥፋተኛ የሚከፍለው ገንዘብ ወይም ሌላ ነገር። *ያለብህን እዳ በወቅቱ ካላጠናቀቅህ መቀጫ ትከፍላለህ።*

መቀጫ ጣለ ቅጣት በየነ፤ ወሰነ።

መቀጣጫ ስ 1. ጥፋቱ ወይም ስህተቱ ዳግም እንዳይፈፀምና ለአጥፊውም ሆነ ለሌላው ሰው ትምህርት (ማስፈራሪያ) እንዲሆን የተሰጠ ወይም የሚሰጥ ከባድ ቅጣት። 2. መዘባበቻ።

ቀጣሪ "ቀጠረ" ስር ተመ.

ቀጣኚት ስ ትንሽ ጉልማ መሬት።

ቀጣና ስ 1. በገደልና በገደል መካከል ያለ የሰውና የከብት መሄጃ፡ መተላለፊያ ቀጭን መንገድ። 2. የተወሰኑ ቦታዎችን ወይም አካባቢዎችን የሚያጠቃልል መልክአምድራዊ ክልል።

ቀጣጠለ "ቀጠለ" ስር ተመ.

ቀጣጠፈ "ቀጠፈ" ስር ተመ.

ቀጣጥይ "ቅጣጥይ" ን ተመ.

ቀጣፊ "ቀጠፈ^{2}" ስር ተመ.

ቀጤማ "ቄጠማ" ን ተመ.

ቀጥ

ቀጥታ ቅ ጠማማ ወይም ወልጋዳ ያልሆነ።

[በ] ቀጥታ ተው.ግ. ወደሌላ ቦታ ሳይሄድ። *በቀጥታ ወደ ስራ ላስኪያጅ ቢሮ ሄደ።* 2. ፊት ለፊት፡ በግልፅ፡ ሳይድበሰበስ (ቅኔነት፡ አሽሙር፡... በሌለበት አነጋገር)። *ምክንያቱን ከምታውቀው በቀጥታ ለምን አልቻልም አትልም?*

ቀጥታ ስልክ ስ በማዞሪያ በኩል ያልሆነ፡ ወደተፈለገበት ቦታ በቀጥታ መደወል የሚያስችል ስልክ።

ቀጥተኛ ቅ ያልተጣመመ፤ ያልተወላገደ፡ ትክክለኛ የሆነ (መስመር፡ መንገድ፡...)። 2. ግልፅ የሆነ፡ እውነተኛ፤ ትክክለኛ (ሰው)። 3. በሌላ በኩል ወይም በተዘዋዋሪ ያልሆነ። *በመካከላችን ቀጥተኛ ግንኙነት አለ።*

ቀጥ አለ ግ 1. ቆመ፡ ተገተረ። 2. መንቀሳቀሱን ተወ፡ ረጋ። 3. ጎብጦ፤ ተጣሞ፡ ተወላግዶ የነበረው ተስተካከለ፡ ቀና። 4. ስነስርአት ያዘ (በቅጣት፤ በተግሳፅ፡ በምክር፡...የተነሳ)። 5. መስራት አቆመ (በብልሽት ወይም በሌላ ምክንያት)። *ሰአቴ ቀጥ አለች።* 6. ተቋረጠ፡ ቆመ፡ ተወ። *ዝናቡ ቀጥ አለ።* 7. መንገዳገዱን ተወ፤ ሚዛኑን ጠበቀ። *ህፃኑ ቀጥ ብሎ መሄድ ጀመረ።*

ቀጥ ብሎ ተው.ግ. ወዲያ ወዲህ ሳይል፤ ሳያመነታ። *ቀጥ ብሎ ወደ ትምህርት ቤት ሄደ።*

ቀጥ አደረገ ግ 1. አቆመ፡ ገተረ። 2. እንዳይንቀሳቀስ አደረገ። 3. ጎብጦ፡ ተጣሞ፤ ተወላግዶ የነበረውን አስተካከለ፡ አቃና። 4. ስነስርአት አስያዘ (በመቅጣት፤ በመገሰፅ፤ በመምከር፡...)። 5. እንዳይሰራ አደረገ። *ሞተሩን ቀጥ አደረገው።* 6. አቋረጠ፡ አቆመ፡ አስተወ። *መድሃኒቱ ሳሉን ቀጥ አደረገለት።*

ቀጥ አድርጎ በደንብ አስተካክሎ፡ ያለችግር። *ስራውን ቀጥ አድርጎ የሚሰራው እሱ ነው።*

ቀጥቃጣ "*ቀጠቀጠ" ስር ተመ.

ቀጥቃጭ "ቀጠቀጠ" ስር ተመ.

ቀጨ^{1} ግ 1. አክርማን፤ ስንደዶን ከአንጓው ወይም ከቅልጥሙ ላይ እየሰበረ ሰበሰበ። 2. በአያያዝ ጉድለት ወይም በሌላ አደጋ የአካል መገጣጠሚያ፤ የስር መዞር፤ ወለምታ፤... አደረሰ። *ህፃኑን ስትሸከም በጥንቃቄ ካላነሳሀው ልትቀጨው ትችላለህ።* 3. (ዘይ.) ሀ- ቀበረ፤ ገደለ (በልጅነት)። ለ- ከመጀመሪያው በአጭሩ አስቀረ፡ አሳጠረ (ነገርን፤ ሃሳብን፤...)።

ቅጭት ስ በአያያዝ ጉድለት ወይም በሌላ

አደጋ የደረሰ የአካል መናጋት፥ የስር መዛር፥ ወለምታ።

ተቀጨ ገ 1. በእያያዝ ጉድለት ወይም በሌላ አደጋ የአካል መናጋት፥ የስር መዛር፡ ወለምታ፥ ... ደረሰበት። 2. (ዘይ.) ሀ-ተቀሰፈ፡ በልጅነት፥ ያለእድሜው ሞተ። ለ-ከመጀመሪያው በአጭሩ እንዲቀር ተደረገ (ሃሳብ፥ ነገር፣...)።

ቀጨ^{2} ገ እጅን፥ ክንፈርን፥...በንግጠቀ፡ ስንታተረ (ብርዱ፥ ውርጩ፥...)።

ቀጭ ስ በብርድ፥ በውርጭ የሚመጣ የእጅ፡ የከንፈር፣...መሰንጣጠቅ።

ቀጨለ "ቃጨለ" ን ተመ.

ቀጨመ ገ ቅጫም ያዘ፥ አፈረ።

ቅጫም(ቅማጭ) ስ የጤፍ ፍሬ የሚያክልና ነጣ ያለ የቅማል እንቁላል።

ቅጫማም ቅ (ስድብ) ቅጫም ያለበት፥ ንፅህናውን የማይጠብቅ።

***ቀጨመ**^{1}

ቀጨማ(የቀጨማ) ስ የጠፋ ከብት ይዞ ላመጣ ወይም ላሳደረ፣... የከብቱ ባለቤት የሚከፍለው ገንዘብ፡ የጅብ አፍም ይባላል።

ቀጨም አደረገ ገ አፈፍ፡ ለቀም አደረገ፡ ያዘ።

***ቀጨመ**^{2}

ቅጭም አለ ገ ከሃዘን፡ ከድንጋጤ፣... የተነሳ ፊቱ ኩስትር፥ ቁጥር፥ ቅይም የማለት ወይም የመከፋት መልክ አሳየ።

አቀጨመ ገ ከሃዘን፡ ከድንጋጤ፣... የተነሳ ፊቱን አከፋ፥ አጠቆረ፡ ቋጠረ።

ቀጨሞ ስ ፍሬው ሲቀምሱት የሚኮመጠጥና የኮሶ መድሃኒት ነው የሚባል የእፀዋት አይነት።

ቀጨቀጨ ገ 1. በጥርሱ ሰባበረ፡ አደቀቀ፡ ፈጨ። 2. ደጋግሞ ነከሰ፥ በላ።

ተንቀጫቀጨ ገ 1. እርስ በርሱ በመገጫጨት ወይም በንቅናቄ የተነሳ ቀጭ ቀጭ የሚል ድምፅ ሰጠ (ብረታ ብረት፥...)።

አንቀጫቀጨ ገ እርስ በርስ በማጋጨት ወይም በማንቃነቅ ቀጭ ቀጭ የሚል ድምፅ እንዲሰጥ አደረገ።

ቀጨጨ ገ በሚገባው መጠን ሳያድግ፥ ሳይጠፍር ቀረ።

ቀጫጫ ቅ 1. ክስማና፡ ኮሳሳ፥ ደቃቃ (ለእፀዋት)። 2.(ስድብ) አጭር፡ ቀጭን (ለሰው)።

ቀጭ "ቀጨ^{2}**"** ስር ተመ.

ቀጭ

ቀጭ አለ (እቀጭ አለ) ገ ምስማር በመዶሻ ሲመታ፡ ድንጋይና ድንጋይ ሲጋጭ፡ ደረቅ እንጨት ሲሰበር፣... የሚሰጠውን አይነት ድምፅ ሰጠ።

ቀጭ አደረገ (እቅጭ አደረገ) ገ ድንጋይና ድንጋይ ሲጋጭ፡ ደረቅ እንጨት ሲሰበር የሚሰጠውን አይነት ድምፅ እንዲሰጥ አደረገ።

ቀጭ ቀጭ አደረገ ገ 1. ቆረጠመ (ቆሎን)። 2. መታ፡ ቀጠቀጠ (ለምሳሌ ምስማርን፡ ቆርቆሮን፥...)።

ቀጭ ቀንቧ አለ የአካሄድ ሁኔታን ለመግለፅ የሚነገር ቃል። *ቀጭ ቀንቧ እያለች መጣች።*

ቀጭቋ አለ (እቀጭ እቋ አለ) በቀጭኑ የሚሰማን የጫማ ኮቴ ድምፅ አይነት አሰማ።

ቀጭኔ ስ ቁመቱ ከአራዊት ሁሉ የሚበልጥ፡ አንገቱ ብቻ ሁለት ሜትር ያህል የሚረዝም፡ ቆዳና ፀጉር የለበሱ ሁለት ቀንዶች፥ ረዥም ፀጉር ያለው ጭራ፡ ከረር ያለ ሻካራ ጋማ፡ ሰንጥቅ ሸሆና፡ ግንባሩ ላይ ቀንድ መሰል ነገር ወይም ጉንቁል ያለው ቀላ ያለ ቡናማ ሆኖ ነጣ ያሉ መስመሮች የተሰበጣጠሩበት ዥንጉርጉር መልክ ያለው፡ የዛፍ ቅጠቋጠና ሳር የሚመገብና በአፍሪካ የሚገኝ ታላቅ የዱር እንስሳ(ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።

ቀጭን "ቀጠነ" ስር ተመ.

ቀፀሰ ገ 1. የተማረውን መንፈሳዊ ትምህርት እንዳይረሳው በየጊዜው መላልሶ አነበበ፡ ደገመ፡ አዜመ። 2. ተማረ፡ አጠና። *ድጓ የቀፀሰው በልጅነቱ ነው።*

ቅፀላ ስ (ቤ.ክህ.) ጥናት።

አስቀፀለ (አስቀጠለ) ገ መንፈሳዊ ትምህርትን አስተማረ፡ አስጠና።

ቀፀላ ስ ካህናት በራሳቸው ላይ የሚጠመጥሙት ወይም ለፊት መሸፈኛ የሚያደርጉት ስስ ሻሽ።

ቀፈረ ገ ጆሮን አቆመ፡ ዘረጋ፥ ቀሰረ፡ አቀና (ለማዳመጥ)።

***ቀፈረረ**

ቀፍራራ(ቀፈረር) ቅ 1. ርዝማኔው የሚያስቀይም። 2 ከርፋፋ።3. ከፍራራ።

ቅፍርር አለ ገ 1.ተንቀፈረረ፥ በሚያስቀይም ሁኔታ ረዘመ። 2. ተንከፈረረ።

ተንቀፈረረ ገ 1. በሚያስቀይም ሁኔታ በጣም ረዘመ። 2. ተንከረፈፈ። 3. ተንከፈረረ።

አንቀፈረረ ገ 1. በሚያስቀይም ሁኔታ በጣም አረዘመ። 2. አንከረፈፈ። 3.አንከፈረረ።

ቀፈቀፈ ገ 1. (ዘይ.) ብዙ ወለደ። 2. ጠረበ፡ ከረከረ (እንጨትን...) 3. መለመለ (የዛፍ ክንፍን፥ ቅርንጫፍን፣...)።

ቀፈቀፈች ገ የታቀፈችውን እንቁላል ፈለፈለች፥ ጫጩት አወጣች(ዶሮ)።

መቀፍቀፊያ ስ የሚጠረብበት፥ የሚከረከርበት፥ የሚመለመልበት መጥረቢያ።

ተቀፈቀፈ ግ 1. ተፈለፈለ፥ ወጣ (ጫጩት ከእንቁላል ውስጥ)። 2. በብዛት ተወለደ።

ቀፈታም "**ቀፈት**^{2}" ስር ተመ.

ቀፈት^{1} (**ቀፈድ፥ ቅፍንድ**) ስ ዙሪያውን ችካል የሚወጠርበት የቁርበት ቀጸጸ ወይም ብስ።

ቀፈት^{2} ስ ትልቅ ሆድ፥ ቦርጭ።

ቀፈታም (**ቀፈዳም**) ቅ (ስድብ) 1. ሆደ ዘርጣጣ፥ ቦርጫም። 2. (ዘይ.) በልቶ የማይጠግብ።

ቀፈደደ ግ 1. አጥብቆ አሰረ፥ ጠፈረ። 2. ነፋ፥ ወጠረ፥ ቀበተተ (ሆድን)።

ቅፍድድ (**ቅፍድ**) ቅ የተወጠረ፥ የተቀፈደደ (ሆድ)።

ተንቀፈደደ ግ ሆዱ ትልቅ ሆነ፥ ተንዘረጠጠ።

***ቀፈደደ**

ቀፈደድ (**ቀፍዳዳ**) ቅ (ስድብ) ፍጥነት፥ ቅልጥፍና የሌለው፥ ከርፋፋ።

ተንቀፈደደ ግ ተንከረፈፈ።

አንቀፈደደ ግ አንከረፈፈ።

እንቅፍድ ቅ (ስድብ) የተንቀፈደደ፥ ከርፋፋ።

ቀፈዳም "**ቀፈት**^{2}" ስር ተመ.

ቀፈድ "**ቀፈት**^{1}" ን ተመ.

ቀፈፈ^{1} ግ ጫፍ ጫፉን በመቁረጥ አስተካከለ፥ ከረከመ (ብራናን፥ ቆዳን፥ ቅልን፥...)

ቅፈፍ ስ 1. ተከርክሞ የወጣ ቁራጭ (የብራና፥ የቁርበት፥ የቅል፥...) ቁራጭ። 2. አካባቢ፥ ክልል፥ ሰበካ።

ቅፉፍ ቅ ተቆርጦ የወጣ፥ ቁራጭ።

ቀፈፈ^{2} ግ መንደር ለመንደር እየዞረ የእለት ጉርሱን ለመነ፥ ሰበሰበ (የቆሎ ተማሪ፥ ለማኝ)።

ቀፈፋ ስ ምግብ ለማግኘት መንደር ለመንደር እየዞሩ የሚደረግ ልመና።

ቀፋፊ ቅ ለማኝ።

አቀፈፈ ግ አለመነ፥ ተዘከረ፥ ለለማኝ ሰጠ።

ቀፈፈ^{3} ግ ስሜትን፥ ሰውነትን ደስ አልል አለ፥ አስጠላ፥ ጨፈገገ፥ ከበደ።

ቀፋፊ ቅ (ስድብ) ደስ የማይል፥ አስጠሊታ፥ አስቀያሚ።

ቀፈፋ "**ቀፈፈ**^{2}" ስር ተመ.

ቀፋፊ^{1} ዝ.ከ.

ቀፋፊ^{2} "**ቀፈፈ**^{3}" ስር ተመ.

ቀፍራራ "***ቀፈረረ**" ስር ተመ.

ቀፍዳዳ "***ቀፈደደ**" ስር "**ቀፈደድ**" ን ተመ.

ቀፎ ስ 1. ከመቃ፥ ከሃረግ ወይም ከቀጫጭን እንጨት (ከቀጨሞ፥ ከከትክታ፥...) ተወሳስቦ የሚሰራ የንብ ቤት። 2. (ዘይ.) ውስጡ ክፍት፥ ባዶ ነገር።



ቀፎ 1ኛ ፍቺ

ቀፎ ለቀፎ ስ.ግ ለስ.ግ፥ ውስጥ ለውስጥ። *ሰውየውን የመታው ጥይት ቀፎ ለቀፎ ሄዶ ስለወጣ አጥንቱ ደህና ነው፥ አልተሰበረም።*

ቀፎ ቆራጭ ስ ከቀፎ ውስጥ ማርን የሚቆርጥ ሰው።

ቁ የ"**ቀ**" ፊደል ካእብ ዘር።

ቁላ ስ 1. (ነውር) የሰውና የእንስሳ ወንድ አባለዘር፥ የወንድ ብልት ዘንግ፥ ወይም ዘንጉና ፍሬዎቹ ባንድ ላይ (ስእሉን ሰውነት ስር ተመ.)። 2. መቀርቀሪያ፥ የመዝጊያ መወርወሪያ። *የመዝጊያ ቁላ፥* 3. ለመደወያ እንዲያገለግል በደወልና በቃጭል ጉያ የሚንጠለጠል ብረት። *የመረዋ ቁላ፥*

ቁላ ቀረሽ (ነውር) ወንዳወንድ የሆነች ሴት።

የቁላ ከብት ስ ያልተወቀጠ፥ ያልተኮላሸ ከብት።

ቁሌታም "**ቆላ**^{1}" ስር ተመ.

ቁሌት ዝ.ከ.

ቁልል "**ቆለለ**" ስር ተመ.

ቁልልታ ዝ.ከ.

ቁልምጫ "***ቆለመጠ**" ስር ተመ.

ቁልቁለት "***ቆለቆለ**" ስር ተመ.

ቁልቁል ዝ.ከ.

ቁልቋል ስ 1. በቆላና በወይና ደጋ የሚበቅልና የሚበላ ፍሬ ያለው እሾሃም የእፅዋት አይነት፥ የባህር ቁልቋልና መንክ ቁልቋልም ይባላል። 2. በቆላና በወይና ደጋ የሚበቅል፥ ወተት የሚመስል ፈሳሽ የሚወጣው፥ እሾህ ያለው



ቁልቋል 2ኛ ፍቺ

ወይም የሌለው የእፀዋት አይነት።

ቁልቢጥ ስ ከቁና የሚያንስ የእህል መስፈሪያ፣ ቃጢ።

ቁልጭልጭ "*ቆለጨ" ስር ተመ.

ቁልፍ "ቆለፈ" ስር ተመ.

ቁልፍልፍ ገ.ከ.

ቁመት "ቆመ" ስር ተመ.

ቁመና ገ.ከ.

ቁማር "ቆመረ" ስር ተመ.

ቁማርተኛ ገ.ከ.

ቁም "ቆመ" ስር ተመ.

ቁምጣ "ቆመጠ" ስር ተመ.

ቁምጤ ስ አንጓ ያለውና እንደ በርድ መሬት ላይ የሚተኛ የሳር አይነት።

ቁምጥማጭ "ቆመጠ" ስር ተመ.

ቁምጥምጥ ገ.ከ.

ቁምጥና ገ.ከ.

ቁምጭር (ቁንጭር) ስ ሽማኔ ጫፉ ላይ ብስ ያለውን የሽማ መጠቅለያ እንጨት የሚሰካበት እናቱ ሹል የሆነ አጭር ችካል(ስእሉን ሽማኔ ስር ተመ.)።

ቁረን(ቆረን) "ቆረነ" ስር "ቆረን"ን ተመ.

ቁረንጮ (ቁርንጮ፥ ቆረንጮ) ስ ያለቀ፥ የደቀቀ አሮጌ ዝተት፣ እላቂ ጨርቅ ወይም ደላጎ።

ቁረት ስ ተቀማጭ ገንዘብ፣ ቅርስ፣ ጥሪት።

ቁራ ስ ድፍን ጥቁር ወይም በጀርባውና በደረቱ ላይ ወይም በራሱ ላይ ብቻ ነጭ ያለበት የአሞራ አይነት(ስእሉን አሞራ ስር ተመ.)።

ቁራ ይጮህበታል ባዶ፥ ጠፍ ነው (ቦታ፥ አገር)።

የቁራ መላኩተኛ ተልኮ የማይመለስ፥ በዚያው የሚቀር።

የቁራ ጩሀት ሰሚ የሌለው ጩሀት፣ እቤቱታ።

የቁራ ምስ ስ ፍሬው ሲበስል ቀይ የሚሆን የሃረግ አይነት፣ የአሞራ ምሳም ይባላል።

የቁራ ወስፌ ስ የእፀዋት አይነት።

ቁራሽ "ቆረሰ" ስር ተመ.

ቁራን "ቁርአን" ን ተመ.

ቁራኛ "*ቆረኘ" ስር ተመ.

ቁራጪም "ቆረጠ" ስር ተመ.

ቁራጭ ገ.ከ.

ቁሬማ ስ 1. እህል የማያበቅል መሬት። 2. (ዘዩ.) ጨብጣ፥ አይን የማይገባ አጭር (ሰው)።

ቁር^{1} ስ የብረት ቆብ።

ቁር^{2}

ቁር አለ ግ በገበጣ ጨዋታ ላይ አንድ ጠጠር ሲይዝና ባዶ ቤት ሲያጋጥመው ጠጠሮን አስቀምጦ አረፈ፥ ተራ ለሌላው ሰጠ።

ቁር^{3} "ቆረረ^{2}" ስር ተመ.

ቁርምቢ "ቁርንቢ" ን ተመ.

ቁርምባጥ "ኩርምባጥ" ን ተመ.

ቁርስ "ቆረሰ" ስር ተመ.

ቁርስራሽ ገ.ከ.

ቁርሾ (ቅርሾ) ስ ቂም።

ቁርሾ ያዘ ቂም ያዘ።

ቁርቁምባ ስ ከገመድ የተሰራ ጠርሙስ መሰል የአሳ መያዣ።

ቁርቁራ ስ ፍሬው የሚበላ፥ በቆላ አካባቢ የሚበቅል እሾህ ያለው ዛፍ፣ ፍሬውም ቁርቁራ ይባላል።

ቁርቆሳ "ቆረቆሰ^{1}" ስር ተመ.

ቁርበት ስ 1. የተለፋ የከብት ቆዳ። 2. የገላ ቆዳ (ሽፋን)።

ቁርበተ ሞኝ ለማያውቀው ሰው ሲያዩት ሞኝ የሚመስል (ሰው)።

ቁርበት ፋቂ "ፋቀ" ስር "ፋቂ" ን ተመ.

ቁርባ (ቁርምባ) ስ የሚያስታውክ፥ የሚያስቀምጥ፥ ሰውነትን የሚያደርቅ ድንገተኛ በሽታ።

ቁርባብቻ "*ቆረበበ" ስር "ቆርባብቻ" ን ተመ.

ቁርባን "ቆረበ" ስር ተመ.

ቁርብቻ "*ቆረበበ"ስር "ቆርባብቻ"ን ተመ.

ቁርብጭታ "ቆረበጨ" ስር ተመ.

ቁርንቢ (ቁርምቢ) ስ ለመታረድ የደረሰ የፍየል ወጠጤ።

ቁርንባጥ "ኩርንባጥ" ን ተመ.

ቁርንዳድ (ቁርንድድ) ቅ ቁርንጭጭ፥ ከርዳዳ፥ ቁጥርጥር (ፀጉር)።

ቁርንጫጭ ቅ 1. ቁርንዳድ፥ ከርዳዳ፥ ቁጥርጥር (ፀጉር)። 2. (ዘዩ.) ንጭንጫ (በአመል)።

ቁርንጮ "ቁረንጮ" ን ተመ.

ቁርንፋድ "ቅርንፋድ" ን ተመ.

ቁርአን (ቁራን) ስ የእስልምና ሃይማኖት ቅዱስ መፅሃፍ።

ቁርዝ ስ 1. የበሬ ወይም የወይፈን ብልት (አባለዘር)። 2. ወሸላ፣ ያልተገረዘ የወንድ ብልት።

ቁርዛም ቅ (ስድብ) ወሸላ።

ቁርጬ ስ እግረ ረዥም አሞራ፤ ሽመላ (በብዛት ሆኖ የሚዘምት)።

ቁርጠት "ቆረጠ" ስር ተመ.

ቁርጠኛ ዝ.ክ.

ቁርጣ ዝ.ክ.

ቁርጥ ዝ.ክ.

ቁርጥማት "ቆረጠመ" ስር ተመ.

ቁርጥራጭ " ቆረጠ" ስር ተመ.

ቁርጩ [ደሃ] ቅ ላንዳች ነገር የሌለው (ሰው)።

ቁርጭምጭሚት ስ በቅልጥምና በጫማ መጋጠሚያ ግራና ቀኝ ከተረከዝ ከፍ ብሎ በስተጎን በኩል የሚገኝ ጉጥ መሰል የሰውነት ክፍል(ስእሉን ሰውነት ስር ተመ.)።

ቁርጭኝ ስ ከትልቅ መፅሃፍ የተውጣጣ አጭር ፅሁፍ።

ቁርፍድ "ቆረፈደ" ስር ተመ.

ቁስ

ቁሳቁስ ስ ልዩ ልዩ የቤት እቃ።

ቁሳዊ ቅ ቁስአካላዊ።

ቁስአካላዊ ቅ (ፍል.) ቁስ አካልን ከሃሳብ ወይም ከህሊና የሚያስቀድም።

ቁስአካላውያን ስ ቁስ አካልን ከሃሳብ ወይም ከህሊና የሚያስቀድሙና ሃሳባዊነትን የሚቃወሙ የፍልስፍና ፈርጅ ተከታዮች።

ቁስአካላዊነት ስ ቁስ አካልን ከሃሳብ ወይም ከህሊና የሚያስቀድምና ሃሳባዊነትን የሚቃረን የፍልስፍና ፈርጅ።

ቁስለት "ቆሰለ" ስር ተመ.

ቁስለኛ ዝ.ክ.

ቁስል ዝ.ክ.

ቁሻሻ "ቆሸሸ" ስር "ቆሻሻ" ን ተመ.

ቁሸቢያም "ቆሸበ" ስር ተመ.

ቁሽብ ዝ.ክ.

ቁቁ

ቁቁታ ስ ኩኩታ፥እሪታ፤ የድረሱልኝ ጩሀት።

ቁቁ አለ ግ ኩኩ፥ እሪ አለ፤ የድረሱልኝ ጩሀት አሰማ።

ቁቅ

ቁቅ አለ ግ ቀጠን ያለ የፈስ ድምፅ ተሰማ።

ቁቅ አደረገ ግ በትንሹ ፈሳ፤ ቀጠን ያለ የፈስ ድምፅ አሰማ።

ቁባት (እቁባት) ስ ቅምጥ፤ ውሽማ።

ቁቤላ ስ የገዞን ጊደር።

ቁብ ስ ደንታ፥ ግድ። *የፈለግሽውን ብትሆን ቁብ የለኝም።*

ቁብየለሽ ቅ ደንታ ቢስ፤ ግድ የለሽ።

ቁብ፟

ቁብ አለ ግ ከፍ ያለ ቦታ ላይ ወይም ፈረስና በቅሎ ጀርባ ላይ ወጣ፥ ተቀመጠ፤ ጉብ አለ።

ቁብ፟ ቁብ፟ አለ ግ የጫማ ኮቴ ድምፅ እያሰማ ተራመደ።

ቁብላ ስ ወይፈን።

ቁቲት (ቁጢት) ስ የነጠላ፥ የጋቢ፥ የኩታ፥…ዘርፍ፤ የሚቋጨው ክፍል።

ቁቲት በጣሽ (የን.እነ.) ሽማኔ።

ቁትቻ "ቆተቸ" ስር ተመ.

ቁቻ ስ የእንጉዳይ አይነት።

ቁና ስ ለእህል መስፈሪያ (መለኪያ) የሚያገለግል የስፌት እቃ(ስእሉን የስፌት እቃ ስር ተመ.)።

ቁናሳም "ቆነሰ" ስር ተመ.

ቁናስ ዝ.ክ.

ቁንቁኔ "ቆነቆነ" ስር ተመ.

ቁንቁን "ቆነቆነ" ስር "ቁንቁኔ" ን ተመ.

ቁንን "ቆነነ" ስር ተመ.

ቁንዲ "ቁንዶ" ን ተመ.

ቁንዳላ "ቆነደለ" ስር ቆንዳላ" ን ተመ.

ቁንድድ "ቆነደደ" ስር ተመ.

ቁንድዶ "ቆነደደ" ስር "ቁንድድ"ን ተመ.

ቁንዶ (ቁንዲ) ቅ ባለሙያ (ሴት)።

ቁንዶ በርበሬ ስ በሻይ፥ በወጥ፥… ውስጥ የሚገባ የቅመም አይነት።

ቁንጅና "ቆነጀ" ስር ተመ.

ቁንጢጥ "ቆነጠጠ" ስር "ቁንጥጫ" ን ተመ.

ቁንጣሪ "ቆነጠረ" ስር ተመ.

ቁንጣሬ ስ ፈንጣ።

ቁንጣን ስ ብዙ ከመብላት የተነሳ ሆድን የሚወጥር፥ የሚያስጨንቅ የህመም ስሜት።

ቁንጣናም ቅ (ስድብ) ያለልክ በልቶ ሆዱ የተነፋ፥ የሚጨነቅ።

ቁንጥር ቁንጥር አለ "*ቆነጠረ" ስር ተመ.

ቁንጥንጥ "*ቆነጠነጠ" ስር ተመ.

ቁንጥጫ "ቆነጠጠ" ስር ተመ.

ቁንጫ "ቆነጨ" ስር ተመ.

ቁንጫጪት "ቁጫጭ" ን ተመ.

ቁንጮር¹ "ቆምጮር" ን ተመ.

ቁንጮር² (ጮንቁር) ስ አብዛኛውን ጊዜ በጉንጭና በአፍንጫ አካባቢ የሚወጣ የቁስል አይነት፤ ሻህኝ።

ቁንጮ ስ 1. ዙሪያውን ከተላጨ በኋላ መሃል አናት ላይ የሚቀር የልጅ ፀጉር። 2. የሳር ቤት ክዳን አናት (ጉልላት የሚቀመጥበት)። 3.(ዘይ.) ዋንኛ፣ የበላይ፣ ታዋቂ፣...።

ቁንፀል "ቆነፀለ" ስር ተመ.

ቁዘማ "ቆዘመ" ስር ተመ.

ቁዝር "ቆዘረ" ስር ተመ.

ቁዳማ "አቁማዳ" ን ተመ

ቁጊያም (ቁጋም) "ቆጋ" ስር ተመ.

ቁግ ዝ.ከ.

ቁጠባ "ቆጠበ" ስር ተመ.

ቁጡ "*ቆጣ" ስር ተመ.

ቁጢ ስ የቡና ቅጠል (ሲደርቅ ታምሶ እንደ ሻይ ቅጠል ተፈልቶ የሚጠጣ)፤ መጠጡም ቁጢ ይባላል።

ቁጢሳ "ኩቲሳ" ን ተመ.

ቁጢት "ቁቲት" ን ተመ.

ቁጢጥ አለ "ቆጠጠ" ስር ተመ.

ቁጣ "*ቆጣ" ስር ተመ.

ቁጣጥ "ቆጠጠ" ስር ተመ.

ቁጥር "ቆጠረ" ስር ተመ.

ቁጥር "ቋጠረ" ስር ተመ.

ቁጥርጥር ዝ.ከ.

ቁጥቋጦ "ቆጠቆጠ" ስር ተመ.

ቁጥብ "ቆጠበ" ስር ተመ.

ቁጥጥር "ቆጠረ" ስር ተመ.

ቁጨት "ቋጨ" ስር ተመ.

ቁጫጭ (**ቁንጫጪት**) ስ መጠኑ አነስተኛ የሆነ፣ መልኩና ቅርጹ ትንኝን የሚመስል ነፍሳት።

ቁጭ

ቁጭ ብድግ አለ 1. ተሽቆጠቆጠ፣ ወዲያ ወዲህ አለ (እንግዳን ለማስተናገድ)። 2. ተንቆራጠጠ።

ቁጭ ነው በጣም ይመስላል (ከ ___ ጋር አንድ አይነት ነው ለማለት የሚነገር)። *አሁን የተወለደው ልጅ አባቱን ቁጭ ነው።*

ቁጭ አለ ግ ተቀመጠ፣ ኖረ።

ቁጭ ብዬ ስ አጭር የማሽላ አይነት።

ቁጭ አደረገ ግ አስቀመጠ፣ አኖረ።

ቁጭት "ቆጨ" ስር ተመ.

ቁፋሮ "ቆፈረ" ስር ተመ.

ቁፍ

ቁፍ አለች ግ እንቁላል መጣል አቅማ ተቀመጠች፤ ጭር አለች፣ ጭክ አለች (ዶሮ)።

ቁፍ ቁፍ አለች ግ ቁፍ ቁፍ የሚል ድምፅ አሰማች፣ ጨከከች (ዶሮ)።

ቂ የ"ቀ" ፊደል ሳልስ ዘር።

ቂላቂል "ቄለ" ስር ተመ.

ቂል ዝ.ከ.

ቂመኛ "*ቀየመ" ስር ተመ.

ቂም ዝ.ከ.

ቂብ

ቂብ አለ ግ 1. ቁብ፣ ጉብ አለ። 2. ቁጢጥ አለ።

ቂን

ቂን ቂን አለች ግ (ተራ.አነ.) ልታይ ልታይ አለች።

ቂንድ ስ የማሽላን፣ የበቆሎን፣... ፍሬ ከቆረቆንዳው ጋር የሚያያዘው ክፍል።

ቂንጥር ስ (ነውር) 1. በሴት ብልት አፍ አካባቢ በላይ በኩል የሚገኝ ቆም ያለ እንጥል መሰል አካል። 2. የሴት አባለ ዘር፣ ብልት።

ቂንጥራም ቅ (ነውር፣ ስድብ) ደካማ፣ ፈሪ፣... ለማለት የሚነገር።

ቂጣ ስ 1.ዱቄት በወፍራሙ በውሃ ተለውሶ ሳይቦካ ወዲያውኑ የሚጋገር የምግብ አይነት። 2. በደንብ ያልተጋገረና አይን የሌለው እንጀራ። 3. ወፍራም፣ ፊተ ክብ። *ቂጣ ፊት ነው።* 4. (ዘይ.) በአስተሳሰቡ ያልበሰለ (ሰው)።

ቂጥ ስ 1. ከወገብ በታች በስተኋላ በኩል ወጣ ብሎ የሚታይ የአካል ክፍል (ስእሉን ሰውነት ስር ተመ.)። 2. አካላዊ የኩስ መውጫ፣ ፊንጢጣ። 3. እንደ እንስራ፣ ብርሌ፣ ጣባ፣ ብርጭቆ፣... ያሉ እቃዎች የታችኛ ክፍል፣ መቀመጫ። 4. የመጨረሻ፣ የታችኛ ክፍል። *የሸንኮራ አገዳ ቂጥ።*

ቂጡ ቄጠማ ቆረጠ 1. ከፍርሃት የተነሳ ሰውነቱ ራደ፣ ተንቀጠቀጠ። 2. በጣም ተደሰተ።

ቂጡን ጣለ 1. ልብሱ ተቀዶ ሰውነቱ ታየ (በተለይ ከወደቂጡ)። 2. አጣ ነጣ፣ ደኸየ።

ቂጥ ለቂጥ ገጠመ ተስማማ፣ አበረ፣ አብሮ ሆነ (ለማደም፣ ለማሴር፣...)

ቂጥ ሳበ (ነውር፣ የጓ. አነ.) ተለማመጠ።

ቂጣም ቅ ቂጠ ትልቅ።

ቂቾ

ቂጥ አለ ግ ከፍ ባለ ቦታ ላይ ተቀመጠ፡ ቁብ አለ።

ቂጥጥ አለ ዝ.ከ.

ቂጥ አደረገ ግ ከፍ ባለ ቦታ ላይ አስቀመጠ ፥ አኖረ።

ቂጥጥ አደረገ ዝ.ከ.

ቂጥኝ ስ ተላላፊ ከሆኑና ሰውነትን ከሚያቆሳስሉ የአባለዘር በሽታዎች አንዱ።

ቂጥኛም ቅ (ስድብ) ቂጥኝ ያለበት፡ የያዘው።

ቃ^{1} የ"ቀ" ፊደል ራብእ ዘር።

ቃ^{2}

ቃ አለ ግ 1. ደረቅ፡ ቀንበር፡ በሰል አለ (ለቂጣ፡ ለዳቦ)። 2. በመሰበር፡ በመጋጨት፥... "ቃ" የሚል ድምፅ አሰማ።

ቃ አደረገ ግ 1. ደረቅ፡ ቀንበር፡ በሰል አደረገ (ለቂጣ፡ ለዳቦ)። 2. በመሰበር፥ በመጋጨት፥..."ቃ" የሚል ድምፅ እንዲሰማ አደረገ።

ቃቃ አለ ግ "ቃቃ" የሚል ድምፅ አሰማ።

ቃቃ አደረገ ግ "ቃቃ" የሚል ድምፅ እንዲሰማ አደረገ።

ቃቃታ ስ "ቃቃ" የሚል ድምፅ፥ ኳኳታ።

ተንቃቃ ግ 1. እሳት ወይም ፀሃይ ላይ ቆየ፥ ደረቀ፥ ቀነበረ። 2. "ቃቃ" የሚል ድምፅ ሰጠ፤ ተንቋቋ። 3. የተወሰነ ቦታ ላይ ሆኖ አንድን ነገር ረዘም ላለ ጊዜ በመጠበቅ ተንገላታ፥ ተበቃየ። *እሱ ይመጣል ብዬ በመጠበቅ ብዙ ተንቃቃሁ።*

አንቃቃ ግ 1. ከሳት ወይም ከፀሃይ ላይ አቆየ፡ አደረቀ፡ አቀነበረ። 2. "ቃቃ" የሚል ድምፅ እንዲሰጥ አደረገ፤ አንቋቋ። 3. አስቆየ፥ አስጠበቀ፥ አንገላታ። *በቀጠሮው ሰዓት ባለመገኘቱ እንግዶቹን ፀሃይ ላይ አንቃቃቸው።*

ቃሰቀንዳ "ቀሰቀንዳ"ን ተመ.

ቃሰአጤ "ቀሳጤ"ን ተመ.

ቃሊም^{1} ስ የወንዝ ወይም የጅረት ዳር፥ ደገፍ፤ ከከንፈሩ እስከ ውሃው ያለው ቦታ፤ ድንጋግ።

ቃሊም^{2} **(ቃሊብ)** ስ በትንባሆ መጠጫ (በጋያ) አናት ላይ ያለው የትንባሆና የእሳት ማስቀመጫ።

ቃል (ብ.ቁ.**ቃላት**) ስ 1. አንድን ፅንሰ ሃሳብ ለመወከል በድምፅ የተነገረ ወይም በፅሁፍ የሰፈረ የድምፅ ምልክቶች ቅንብር፥ አነስተኛው የአረፍተ ነገር ክፍልፋይ። 2. ስለአንድ ነገር የተባለ፥ የተነገረ፥ የተፃፈ ሃሳብ፡ አስተያየት፡ መልእክት፥...። *ቃሉ የእሱ ነው።* (በነጠ.ቁ.ብቻ) ትእዛዝ፡ መመሪያ። *ልጁ ከአባቱ ቃል አይወጣም ለንጉስ ቃል አይቀርም።* 4. ድምፅ። *ቃሉ ተዘጋግቷል።* 5.እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ። *በመጀመሪያ ቃል ነበረ፥ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፥ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ።*

ቃሉ ተዛነፈ እፈፅማለሁ፥ አደርጋለሁ፥... ያለውን ሳይፈፅም ቀረ።

ቃሉን አከበረ /ጠበቀ 1. እፈፅማለሁ፡ አደርጋለሁ ያለውን ፈፀመ፡ አደረገ፤ በቃሉ ፀና። 2. ትእዛዙን፡መመሪያውን ፈፀመ።

ቃሉን አጎደለ አደርጋለሁ ብሎ የገባውን ቃል አፈረሰ፥ ሳይፈፅም ቀረ።

ቃሉን አጠፈ የተናገረውን ሳይፈፅም ቀረ፡ ካደ።

ቃል ለምድር ለሰማይ በተናገርኩት እፀናለሁ ለማለት የሚነገር መሃላ።

ቃል ለቃል ፊት ለፊት፥ በመነጋገር በመገናኘት። *ለምሽ ተገናኝተው ቃል ለቃል ተነጋግረዋል።*

ቃል ሰጠ 1. ለተጠየቀው ጥያቄ መልስ መለሰ፡ መሰከረ (በፍርድ ቤት፥ በመርማሪ፥...)። 2. ቃል ገባ፥ አረጋገጠ፥ እንደሚያደርግ ተስፋ ሰጠ።

ቃል ተቀበለ ከሳሽ ወይም ተከሳሽ ወይም ምስክር የሰጠውን ቃል፥ ቃል ተቀባዩ መዘገበ።

ቃል ተቀባይ ስ ከሳሽ ወይም ተከሳሽ ወይም ምስክር የሰጠውን ቃል መዝጋቢ፥ ፀሃፊ ።

ቃል አቀባይ ስ ዜና አስተላላፊ።

ቃል አሰረ ተፈጣጠመ፥ ቃለበት አደረገ፤ ቃልኪዳን ገባ (ለጋብቻ)።

ቃል ማሰሪያ ስ ለመጋባት ውል የሚፈፀምበት፡ ቃልኪዳን የሚገባበት፡ ቃለበት የሚደረግበት ስነስርአት፡ ፍጥምጥም።

ቃል አጠረው/አነሰው ሁኔታው ከባድ፥ ጉልህ፥ አስደናቂ፥ አስደሳች፥ ...ከመሆኑ የተነሳ ተመጣጣኝ የሆነ መግለጫ ወይም ቋንቋ አነሰው።

ቃል ገባ አንድ ነገር ለማከናወን ወይም ለመፈፀም ተስማማ፡ ውል ገባ፤ ተስፋ ሰጠ።

ቃልዎ ይድረሰኝ ከቃልዎ አልወጣም፥ ግዝት ይሁንብኝ ለማለት በቄስ ፊት የሚነገር የመሃላ ቃል።

ቃለ መሃላ ስ 1. አንድ ሰው ሲምል የሚናገረው የመሃላ ቃል። 2. አንድን አላማ ከግብ ለማድረስ ወይም አንድን ተግባር በቅንነትና በታማኝነት ለማከናወን ከልብ እንደሚጥሩ ለማረጋገጥ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀ ስነስርአት ላይ የሚገባ ቃል ኪዳን።

ቃለ መሃላ ፈፀመ 1. አንድን ነገር እፈፅማለሁ፡ አደርጋለሁ ብሎ ቃል ገባ። 2. ቃል ኪዳን ገባ።

ቃለ መጠይቅ ስ 1. ስለ አንድ ጉዳይ መረጃ፥ አስተያየት፥ ትምህርት ለማግኘት በሁለት ወገኖች (ጠያቂና ተጠያቂ) መካከል የሚደረግ ጥያቄና መልስ። 2. አንድን ሰራተኛ ለመቅጠር የሚደረግ የቃል ፈተና።

ቃለ ምልልስ ስ 1. ከልዩ ልዩ ጉዳዮች አስተያየት ወይም ትምህርት ለማግኘት በሁለት ወገኖች (ጠያቂና ተጠያቂ) መካከል የሚደረግ ጥያቄና መልስ ያለበት ውይይት። 2. (ፍል.) ክርክር። 3. (ስነ ፅ.) በገፀ ባህርያት መካከል የሚደረግ የንግግር ልውውጥ።

ቃለ ቡራኬ ስ የማሳረጊያ ፀሎት።

ቃለ አጋኖ ስ መገረምን፥ ማጋነንን፥ ማድነቅን፥...የሚያመለክት ቃል። *ላሌት! /ወይ ጉድ!*

የቃለአጋኖ ምልክት ስ የማጋነን ምልክት ስም። ምልክቱም "!" ነው።

ቃለ እግዚአብሄር ስ የእግዚአብሄር ቃል፥ መንፈሳዊ ትምህርት።

ቃለ ጉባኤ ስ የአንድን ስብሰባ ውይይትና ውሳኔ የያዘ ፅሁፍ (ብዙውን ጊዜ የስብሰባውን ቦታ፥ ጊዜና አጀንዳ፥ የአባላት ስም ዝርዝር ይጨምራል)።

ቃለጉባኤ ያዘ/ተቀበለ ግ በስብሰባ ላይ የሚሰነዘሩትን ፍሬ ነገሮች መዘገበ፥ ፃፈ።

ቃል በቃል 1. በተረው እንዳለ፥ ለአንድ ቃል አንድ ትርጉም በመስጠት። 2. የተነገረው ወይም የተፃፈው እንዳለ፥ በሙሉ። *የተነገረውን ሁሉ ቃል በቃል ይዞታል።*

ቃል አባይ ቅ ዋሾ፥ ቀጣፊ፥ ቃሉን የሚያጥፍ።

ቃልኪዳን ስ አንድን ነገር ለማድረግ የተገባ ቃል፥ የተሰጠ ተስፋ።

ቃልኪዳን አሰረ አጨ፥ ለጋብቻ ውለታ ፈፀመ።

ቃልኪዳን ገባ አንድ ነገር ለመፈፀም ተስፋ ሰጠ፥ ውል ገባ።

የቃል ኪዳን ቀለበት ስ የጋብቻ ቀለበት።

የቃላት ልውውጥ የሃይለቃል ምልልስ።

የቃላት አስካክ የቃላት ቅንብር፥ አገባብ።

የቃል ትምህርት ስ (ቤ.ክህ.) በቃል የሚጠና (የሚማሩት) የንባብ፥ የዜማ ትምህርት።

ቃልቻ ስ አውቃለሁ፥ አድናለሁ ባይ፥ ጠንቋይ፥ ባለዛር።

ቃመ ግ 1. በርከት አድርጎ ወደ አፉ አስገባ፥ በላ (ጥሬ-ጥሬን፥ ዱቄትን፥...)። 2. ለበሰ፥ ተሸፈነ (በዱቄት፥ በአመድ፥...)። 3. በላ፥ አኘከ (ጫትን)።

ቃሚ ቅ አዘውትሮ ጫት የሚበላ፥ የጫት ሱሰኛ።

ቃሚያ ስ በአንድ ጊዜ ሊቃም የሚችል መጠን አንድ ጉንጭ የሚሆን እንደ ቆሎ ያለ ምግብ።

ቅሞ (ቃሞ) ስ ብዙውን ጊዜ ጥርስ ለሌላቸው ሰዎች የሚዘጋጅና እየተቃመ የሚበላ በቆሎ መልክ ተሰናድቶ የተፈጨ ግብስ።

አቃመ ግ በብዛት ሰጠ። *ጉሮ አቃመው።*

***ቃረ**

ቃር ስ በጨጓራ መታወክ ወይም በምግብ አለመስማማት የተነሳ በደረት አካባቢ የሚሰማ የማቃጠል ስሜት።

ቃር አያውቅሽ ታሞ የማያውቅ፥ ጤናማ ሆኖ የሚኖር(ሰው)።

አቃረ ግ የቃር ስሜት ተሰማ።

ቃረመ ግ 1. ሰብል ከታጨደ ወይም ከተነቀለ በኋላ የወዳደቀውን ወይም የረገፈውን ዛላ ወይም ፍሬ ከማሳው ላይ ለቀመ፥ ሰበሰበ። 2. ከዚህም ከዚያም ትንሽ ትንሽ ሰበሰበ፥ አጠራቀመ። *ከዘመዶቹ የቃረመውን ገንዘብ ልብስ ገዛበት።* 3. (ዘይ.) አንድ በአንድ፥ ተራ በተራ ሁሉንም ገደለ። *ጠላቶቹን ቃረማቸው።*

ቃራሚ ቅ ቃርሚያ የሚሰበስብ፥ የሚለቅም (ሰው)።

ቃርሚያ (ቀርም፥ ቅራሚ) ስ ሰብል ከታጨደ ወይም ከተነቀለ በኋላ በማሳው ላይ የሚቀረው የወዳደቀ የሰብሉ ዛላ ወይም ፍሬ፤ ተለቅሞ በአንድነት የተከማቸውም ዛላ ወይም ፍሬ ቃርሚያ ይባላል።

ቃርሞሽ ዝ.ክ.

ቃሪያ ስ 1. ያልቀላ፥ ያልበሰለ የበርበሬ እሸት ዛላ፥ ቃሪያ በርበሬም ይባላል። 2. እንጭጭ፥ ገና ያልበሰለ፥ ያልደረሰ (ፍራፍሬ)። 3. (ዘይ.) በአስተሳሰቡ ያልበሰለ (ሰው)።

ቃሪያ በርበሬ ስ የቃሪያን አንደኛ ፍቺ ተመ.

ቃሪያ ጥፊ ስ በውስጥ እጅ ጀርባ ወይም በአይበሉባ የሚደረግ ጥፊ ወይም ምት፥ በተጨማሪ "ጥፊ"ን ተመ.

ቃራሚ "ቃረመ" ስር ተመ.

ቃሬ ስ ከጎንና ከጎን ያለውን ፀጉር ተላጭቶ በመሃል ራስ ከግንባር እስከ ማጅራት የሚወርድ ቁንጮ(ስእሉን ፀጉር አሰራር ስር ተመ.)።

ቃሬዛ ስ 1. ቁስለኛን፥ ሬሳን ወይም ለመሄድ የማይችል ህመምተኛን ተሸክሞ ለማጓጓዝ የሚያገለግል፥ እግር በሌለው አልጋ ቅርፅ የሚዘጋጅ መሸከሚያ፥ ወስካ፥ ወሳንሳ። 2. በሙታን ስም የሚዘጋጅና ፀሎተ ፍትሃት ለሚያደርጉ ካህናት የሚቀርብ ምግብና መጠጥ፥

ድግስ። 3. ከእንጨት ወይም ከሸንበቆ የሚሰራ የድግስ መብሊያ ገበታ። በተጨማሪ አቆልቋይና አውራጅን ተመ.

ቃሬዛ 1ኛ ፍቺ

ቃር "* ቃረ" ስር ተመ.

ቃርሚያ "ቃረመ" ስር ተመ.

ቃርሞሽ ገ.ከ.

***ቃሰተ**

አቃሰተ ግ ከድካም፤ ከስቃይ፤... የተነሳ ሲተነፍስ የመጨነቅ አተነፋፈስ ወይም ድምፅ አሰማ፤ ኣቃተተ።

ቃቃ ግ ነመጀ፤ ሰየ፤ ፈለገ።

ኣቃቃ ግ ኣነመጀ።

***ቃቃረ**

ተቃቃረ ግ ተቀያየመ፤ ተሸካከረ።

አቃቃረ ግ አቀያየመ፤ አሸካከረ።

ቃቃታ "ቃ" ስር ተመ.

ቃቂጻ ስ ግትቻ፤ እሳቂ (የሰፌድ፤ የእንቅብ፤...)።

ቃበዘ ግ አንድ ነገር ለማየት፤ ለመስማት፤... ወዲያና ወዲህ ሄደ፤ ተራወጠ፤ ባከነ።

ቀበዝባዛ (ቅብዝብዝ) ቅ አንድ ነገር ለማየት፤ ለመስማት፤... ወዲያና ወዲህ የሚራሯጥ፤ የሚባክን።

ቅብዝብዝ አለ ግ በጣም ተቅበዘበዘ።

ተቅበዘበዘ ግ ባከነ፤ ባዘነ፤ ናወዘ፤ ወዲያ ወዲህ ተሯሯጠ።

አቅበዘበዘ ግ አባከነ፤ አባዘነ፤ አናወዘ፤ ወዲያና ወዲህ አሯሯጠ።

ቃባ "**ቀባ**" ን ተመ.

ቃብድ "**ቀብድ**" ን ተመ.

ቃተተ ግ 1. የጭንቅ ትንፋሽ ተነፈሰ፤ አቃሰተ። 2. ተንከራተተ፤ ለፋ፤ ደከመ፤ ዞረ።

ቃታ ስ በሩጫ፤ በህመም፤...ምክንያት የሚፈጠር የሲቃ አተነፋፈስ።

አቃተተ ግ 1. ቃተተ፤ አቃሰተ። 2. አለፋ፤ አደከመ፤ አንከራተተ።

ቃተኛ ስ ቅቤና ድልህ (አዋዜ) አንድ ላይ ተለውሶ የተቀባ ትኩስ እንጀራ።

ቃታ^{1} ስ የጠመንጃ፤ የሽጉጥ፤...ጥይት ማስነሻ፤ መተኮሻ(ለእሱን ሽጉጥ ስር ተመ.)።

ቃታ ሳበ ጥይት ተኮሰ።

ቃታ^{2} "**ቃተተ**" ስር ተመ.

ቃና ስ 1. የምግብ፤ የመጠጥ ጣእም። 2. የድምፅ ወይም የሙዚቃ ለዛ፤ ወዘና፤ ጣእም።

ቃና ዘገሊላ ስ 1.ኢየሱስ ክርስቶስ በሰርግ ቤት ተገኝቶ ውሃውን ወደ ወይን ጠጅ በመለወጥ የመጀመሪያውን ተአምር ያደረገበት የቦታ ስም። 2. (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) በቃና ዘገሊላ የተፈፀመውን ተአምር ለማስታወስ በየአመቱ ጥር 12 ቀን የሚከበር በአል።

ቃንዛ ስ የደም ስርን የመጠዝጠዝ፤ የመንዘር ህመም።

ቃኘ^{1} ግ ወዲያና ወዲህ አየ፤ ተመለከተ፤ ማተረ፤ ጎበኘ፤ ሰለለ።

ቅኝት ስ የተወሰነ አካባቢን የማየት፤ የመሰለል ድርጊት።

ተቃኘ ግ ተጎበኘ፤ ተዳሰሰ።

ቃኘ^{2} ግ 1. እንደ ክራር፤ በገና፤... ያሉ የሙዚቃ መሳሪያ ጅማቶች (ክሮች) እያንዳንዳቸው ልዩ ሙዚቃዊ የድምፅ ቃና እንዲኖራቸው፤ ጅማቶቹን በመወጠርና በማላላት ቅንብራቸውን አስተካከለ። 2.በዜማ አለ፤ አሰማ።

ቅኝት ስ 1. የሙዚቃ መሳሪያ ክሮችን በማጥበቅ ወይም በማላላት የሚፈለገውን የድምፅ ቃና እንዲያወጡ የማስተካከል ድርጊት። 2. የሙዚቃ መሳሪያ ክሮች የተቃኙበት የተወሰነ ሙዚቃዊ የድምፅ ስልት (ለምሳሌ አምባሰል፤ ባቲ፤...)።

ተቃኘ ግ ተነቃቃ፤ ተመራ። *አለምርው በመንፈስ ቅዱስ የተቃኘ ደራሲ።*

ቃዛ ስ ስጋ ለመምተር የሚያገለግል የሸንበቆ ስንጣቂ።

ቃዠ ግ 1. የተዘበራረቀና የማይጨበጥ ህልም አየ። 2. በእንቅልፍ ላይ እያለ ጮሀ፤ አላዘነ ወይም አንዳች ነገር ተናገረ። 3. (ዘይ.) ያልተስተካከለ ወይም የተዘበራረቀ ነገር ተናገረ፤ አወራ።

ቅዠት ስ 1. የተዘበራረቀና በትክክል ለማስታወስ የማይቻል ህልም። 2. በእንቅልፍ ላይ እያሉ የማላዘን፤ ጩሀት የማሰማት ወይም አንዳች ነገር የመናገር ድርጊት። 3. (ዘይ.) የተዘበራረቀ፤ የማይጨበጥ ወይም ሊታመን የማይችል ወሬ።

ቅዠታም ቅ (ሰድብ) ዘባራቂ፤ ትክክለኛ ያልሆነ ነገር የሚናገር።

አቃዠ ግ 1. የተዘበራረቀና የማይጨበጥ ህልም አሳየ። 2. በእንቅልፍ ልብ አስጮሀ፤ አስጨነቀ፤ አስለፈለፈ።

ቃዲ ስ 1. በእስልምና ሃይማኖት የሃይማኖቱ ተከታዮች መንፈሳዊ ዳኛ። 2. የሸሪአ ፍርድ ቤት

ዳኛ ወይም እቃቤ ሆነ።

ቃዳ ስ ጎዘም፥ እመም (የተወሰነ የእርሻ መሬት ስፋት፥ ልክ)።

***ቃጠለ**

ቃጠሎ ስ 1. በእሳት የመያያዝና የመንደድ አደጋ። *ቃጠሎው በሀይወትና በንብረት ላይ ጉዳት አደረሰ።* 2.(ዘይ.) ለፍላፊ፥ ምላሰኛ። *ሴትየዋ ቃጠሎ ናት።*

ቅጥል አለ ግ 1. በጣም ተቃጠለ፥ አረረ፥ ከሰለ። 2. በጣም ተበሳጨ፥ ተማረረ፥ ተናደደ፥ ተቆጨ።

ቅጥል አደረገ ግ 1. አቃጠለ፥ አሳረረ፥ አከሰለ። 2. አበሳጨ፥ አስቆጨ፥ አናደደ።

ተቃጠለ ግ 1. በእሳት ነደደ፥ ጋየ፥ ወደመ፥ አረረ፥ ከሰለ። 2. በፀሃይ ብዛት ወይም በውሃ እጦት፥... የተነሳ ደረቀ፥ አረረ (ተክል)። 3.(ዘይ.) በጣም ተናደደ፥ በገነ። 4. የጊዜ ገደቡ ከማለፉ የተነሳ ከአገልግሎት ውጪ ሆነ። *በተወሰነው ቀን ባለመሄዱ ለአስቴዲዮም መግቢያ የገዛው ቲኬት ተቃጠለ።* 5. ተሰቃየ፥ ተንገበገበ (በውሃ ጥም፥ በፍቅር፥...)። 6. በውስጡ ያለው ብርሃን ሰጪ ሽቦ በመርገፉ አምፖሉ ብርሃን መስጠቱን ወይም መብራቱን አቆመ። 7. ተፈጀ፥ ተለበለበ (በእሳት፥ በግለት፥ በበርበሬ፥...)። 8. አላግባብ ባከነ፥ ጠፋ፥ አለቀ (ጊዜ፥ ገንዘብ፥...)። 9. (ዘይ.) በጩሀት፥ በጫጫታ፥... ብዛት ታወከ፥ ተረበሸ። *ሰፈሩ በጫጫታ ተቃጠለ።*

ተቀጣጠለ ግ ተያያዘ፥ ተለኮሰ፥ ጀመረ (እሳት፥ ነገር፥...)።

አቃጠለ ግ 1. አነደደ፥ አጋየ፥ አከሰለ፥ አሳረረ (በእሳት)። 2. ፈጀ፥ ተኮሰ፥ ለበለበ (እሳት፥ በርበሬ፥...)። 3. የፀሃይ ብዛት ወይም የውሃ እጦት አደረቀ፥ አሳረረ (ለምሳሌ ተክልን)። 4. (ዘይ.) አናደደ፥ አበገነ። 5. አንገበገበ (ውሃ ጥም፥ ፍቅር፥...)። 6. አላግባብ አባከነ፥ አጠፋ፥ ጨረሰ (ጊዜን፥ ገንዘብን፥...)። 7. በነገር፥ በጩሀት፥... አወከ፥ ረበሸ።

አቀጣጠለ ግ ለኮሰ፥ አያያዘ (እሳትን፥ ነገርን፥...)።

ቃጣ ግ 1. ፈለገ፥ ከጀለ፥ ዳዳ (አንድ ነገር ለማድረግ)። 2. አንድ ነገር ለማድረግ እጁን አነሳ፥ ሰነዘረ።

ተቃጣ ግ 1.ታለመ፥ ታቀደ። 2. ተሞከረ።

ቃጤ ስ 1. ከቁና አነስ ያለ የእህል መስፈሪያ፥ መለኪያ። 2. ለቆሎ ወይም ለመጠነኛ ምግብ ማቅረቢያ የሚያገለግል አነስተኛ የስፌት እቃ(ስእሉን የስፌት እቃ ስር ተመ.)።

***ቃጨለ(ቀጨለ)**

ቃጭል ስ መሃሉ ላይ ከተንጠለጠለ ትንሽ ብረት ጋር ሲጋጭ የሚጮህ ድምፅ እንዲሰጥ ተደርጎ በዋንጫ ቅርፅ የተበጀ፥ እጀታ ወይም ማንጠልጠያ ጆሮ ያለው አነስተኛ የብረት ወይም የነሃስ መረዋ (ስእሉን የሙዚቃ መሳሪያ ስር ተመ.)።

ቃጭል

ቅጭል አለ ግ አነስተኛ የሆኑ ብረታ ብረቶች ሲጋጩ የሚሰጡትን አይነት ድምፅ ሰጠ።

ቅጭል አደረገ ግ የቃጭል አይነት ድምፅ አሰማ፥ አቃጨለ።

ቅጭልጭል ስ እንደ ጥቃቅን ብረታብረቶች፥ ሰበርባሬ ጠርሙሶች፥... ያሉ ነገሮች እርስ በርስ ሲጋጩ የሚሰጡትን አይነት ድምፅ የሚሰጥ ቁሳቁስ።

ተቃጨለ ግ ተመታ፥ ተደወለ፥ ድምፅ እንዲሰጥ ተደረገ (ደወሉ፥ ቃጭሉ፥...)

ተቅጨለጨለ ግ 1. ተቃጨለ። 2. እርስ በርስ ከመጋጨት የተነሳ ቃጭል የሚሰጠውን አይነት ድምፅ ሰጠ።

አቃጨለ ግ 1. የቃጭሉን እጀታ ወይም ጆሮ ይዞ በመወዝወዝ እንዲጮህ ወይም ድምፅ እንዲሰጥ አደረገ። 2. የቃጭል አይነት ድምፅ ሰጠ፥ አሰማ።

አቅጨለጨለ ግ እንደቃጭል አጮሀ፥ የቃጭል አይነት ድምፅ እንዲሰጥ አደረገ።

ቃጫ ስ ለገመድና ለልዩ ልዩ አገልግሎት የሚውል ጭረት (ቀጫጭን ክር፥ ፀጉር) የሚወጣው የተክል አይነት፥ ከላይ ከተጠቀሰው ተክል የሚገኘው ጭረትም ቃጫ ይባላል።

ቃጭል "ቃጨለ" ስር ተመ.

ቃጭማ ስ ቅጠሉ ሰፋፊ፥ ግንዱ ውስጠ ክፍት፥ ፍሬው ሀይት አዘል የሆነ የአፀዋት አይነት ። ጉሉ እየተባለም ይጠራል።

ቃፊር ስ የጠላትን እንቅስቃሴ ለመሰለልና ለመጠበቅም የተመደበ የጥበቃ ጓድ ወይም ወታደር።

ቈ የ"ቀ" ፈደል ሃምስ ዘር።

ቈለ ግ ሞኝ ሆነ።

ቂል ቅ ሞኝ፥ ጅል።

ቂላቂል ቅ ሞኛ ሞኝ፥ ጅላጅል፥ በቀላሉ

ሊታሰል የማይችል።

አቄለ ግ 1. አሞኘ፤ አታለለ። 2. ሞኝ አደረገ፤ አጀለ።

ቄራ ስ የእርድ ከብቶች፣ በጎች፣... እየተወሰዱ የሚታረዱበት ቦታ፤ እርድ የሚያከናውን ድርጅት።

ቄስ "ቀሰሰ¹" ስር ተመ.

ቄብ ቅ ገና መውለድ ያልጀመረችና ለመውለድ የሚያበቃት የእድሜ ደረጃ ላይ የደረሰች (እንስት ዶሮ፣ በግ፣ ፍየል፣...)።

የቄብ ልጅ ስ 1. ከቄብ በግ ወይም ፍየል፣... የተወለደ ግልገል ወይም ልጅ። 2. (ዘይ.፤ ስድብ) ባለጌ፤ ያልተቀጣ፤ ስነስርአት የሌለው ልጅ።

የቄብ [ዶሮ] እንቁላል ስ ቄብ ዶሮ የጣለችው ወይም የወለደችው እንቁላል።

ቄንጥ ስ 1. የአነጋገር፣ የአለባበስ፣ የአሰራር፣... ለየት ያለ ሁኔታ። 2. አቀቂር።

ቄንጥ አወጣ 1. የተለየ ሁኔታ አበጀ፤ ፈጠረ፤ አሳየ (በአነጋገር፤ በአለባበስ፤...) 2.አቀቂር አወጣ፤ ነቀፈ።

ቄንጠኛ ቅ ዘናጭ፤ በአለባበስ ወይም በሌላ ከሌላው ለየት የሚልበት ነገር ያለው።

ቄንጡ ቅ ሽቅርቅር።

ቄንጠ¹ (ቀንጠ) ስ ትንንሽ ቀዳዳ እሾህ ያለው የዛፍ አይነት።

ቄንጠ² "ቄንጥ" ስር ተመ.

ቄደር ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ቀሳውስት ንስሃ ለሚቀበለው ምእመን የሚያደርጉለት ፀሎትና የንስሃ ጥምቀት፤ የሚፀልዩበት መፅሃፍም [መፅሃፉ] ቄደር ይባላል።

ቄደር ተጠመቀ የንስሃ ጥምቀት ተጠመቀ።

ቄጠማ (ቀጤማ) ስ በወንዝ፤ በምንጭ ዳርና ዳር ወይም ውሃነት ባለው ቦታ ላይ መስል ብሎ የሚበቅል፤ ክብ ቅርፅ ያለውና ወፍራም የሆነ የሳር አይነት።

ቄጦ ስ ቃሪያ።

ቅ የ "ቀ" ፊደል ሳድስ ዘር።

ቅለት "ቀለለ" ስር ተመ.

ቅሉ እንኳን። *ለበላይ ቢያመለክትም ቅሉ ሊሳካለት አልቻለም።*

ቅላት "ቀላ¹" ስር ተመ.

ቅላጥቤ (ቀላጥቤ) ቅ (ስድብ) ከለፍላፊ፤ በነገር ሁሉ አለሁ አለሁ የሚል።

ቅሌ "ቀላ²" ስር ተመ.

ቅሌታም "ቀለለ" ስር ተመ.

ቅሌት ዝ.ከ.

ቅል ስ 1. በውስጡ ትናንሽ የፍሬ ዘሮችን የያዘ፣ ክብና ውስጡ ክፍት የሆነ ትልቅ ፍሬ የሚጥል ወይም የሚያፈራ፤ መሬት ላይ ተንሰራፍቶ ወይም በአጥርና በዛፍ ላይ እየተንጠለጠለ የሚያድግ ሃረግማ የተክል አይነት፤ ፍሬውም ቅል ይባላል። 2. ከዚሁ ፍሬ ለውሃ መቅጃና መያዣ ወይም ለጥራጥሬ፤ ለሽሮ፤ ለድልህ፤ ለቅቤ፤... ማኖሪያ የሚዘጋጅ እቃ፤ ትምቡና፤ ቀምራ።

ቅሌን ጨርቄን አለ ሰበብ፤ ምክንያት አበዛ።

ለየቅል (እየቅል) ተው.ግ. ለየብቻ፤ ለየራስ፤ ለየግል። *ዱባና ቅል አብቃቀሉ ለየቅል።*

ቅል ራስ (ስድብ) የማያመዛዝን፤ አእምሮው ባዶ የሆነ፤ እውቀት የሌለው።

ቅል አንገት ስ መቀንጠቢያ።

ቅልልሞሽ "ቀለበ²" ስር "**ቅልልቦሽ**" ን ተመ.

ቅልልቦሽ "ቀለበ²" ስር ተመ.

ቅልሞሽ "ቀለበ²" ስር "**ቅልቦሽ**" ን ተመ.

ቅልስልስ "*ቀለሰለሰ" ስር ተመ.

ቅልሽልሽታ "*ቀለሸለሸ" ስር ተመ.

ቅልቅል "ቀላቀለ" ስር ተመ.

ቅልበሳ "ቀለበሰ" ስር ተመ.

ቅልብ "ቀለበ¹" ስር ተመ.

ቅልብልብ "*ቀለበለበ" ስር ተመ.

ቅልብሳት "ቀለበሰ" ስር ተመ.

ቅልብሽ

ቅልብሽ አለው አቅለሸለሸው፤ አጥወለወለው፤ ክልብሽ አለው።

ቅልብጭ ያለ "ቀለበጨ" ስር ተመ.

ቅልቦሽ "ቀለበ²" ስር ተመ.

ቅልውጥ "ቀላወጠ" ስር ተመ.

ቅልጣን "ቀለጠ" ስር ተመ.

ቅልጥልጥ ዝ.ከ.

ቅልጥማም "ቀለጠመ" ስር ተመ.

ቅልጥም ዝ.ከ.

ቅልጥጥ "*ቀለጠጠ" ስር ተመ.

ቅልጥፍና "ቀለጠፈ" ስር ተመ.

ቅመማ "ቀመመ" ስር ተመ.

ቅመማ ቅመም ዝ.ከ.

ቅመም ዝ.ከ.

ቅሚያ "ቀማ" ስር ተመ.

ቅማላም "ቀመለ" ስር ተመ.

ቅማል ዝ.ከ.

ቅማት "**ቅማያት**" ን ተመ.

ቅማንጅር (**ቅማንዥር**) ስ በቅንድብ፥ በሽፋል፥... ላይ የሚወጣ እንደ መዥገር የሚጣበቅ ትንንሽ ተባይ፤ ቅጫም።

ቅማንጅራም ቅ (ስድብ) ቅማንጅር የያዘው፤ ያለበት።

ቅማያት (**ቅማት**) ስ የቅድም አያት አባት ወይም እናት፤ ሶስተኛ አያት።

ቅማጫም "***ቀመጠ**" ስር ተመ.

ቅማጭ "***ቀጨመ**" ስር "**ቅጫም**" ን ተመ.

ቅሟጭ "***ቀመጠ**" ስር ተመ.

ቅም

ቅም አላለውም አልበቃውም፤ አልጠቀመውም።

ቅም ቅም አለው ጣመው፥ ጨምር ጨምር አሰኘው።

ቅምሆ ስ እስከጆሮ የሚሰማ የጉሮሮ ህመም፤ ለቅጾ፤ ቶንሲል።

ቅምምጦሽ "**ቀመጠ**" ስር "**ቅምጦሽ**" ን ተመ.

ቅምሻ "**ቀመሰ**" ስር ተመ.

ቅምቅማት "**ቀመቀመ**[1]" ስር ተመ.

ቅምቡርስ "**ቅንቡርስ**" ን ተመ.

ቅምብቻ "**ቅንብቻ**" ን ተመ.

ቅምቦ "**ቅንቦ**" ን ተመ.

ቅምድምድ "***ቀመደመደ**" ስር "**ቀመድማዳ**" ን ተመ.

ቅምጥ "**አይን**" ስር "**አይናር**"ን ተመ.

ቅሞጥ "***ቀመጠ**" ስር ተመ.

ቅምጥል "***ቀማጠለ**" ስር ተመ.

ቅምጦሽ "***ቀመጠ**" ስር ተመ.

ቅምጫና የ "**ቅል**" ን ሁለተኛ ፍቺ ተመ.

ቅሞ (**ቃሞ**) ስ ፍሬው የሚበላ የእፀዋት አይነት፤ ፍሬውም ቅሞ ተብሎ ይጠራል።

ቅሬላ ስ ለመጫኛ፤ ለጠፍር፥...የሚያገለግል የተሰፋ የበሬ ቆዳ።

ቅሬት "**ቀረ**" ስር ተመ.

ቅራሚ "**ቃረመ**" ስር ተመ.

ቅራሞ ዝ.ክ.

ቅራሪ "**ቀረረ**" ስር ተመ.

ቅራቅንቦ ስ ኩሳንኩስ፤ ኮተት።

ቅራተኛ "**ቀራ**[1]" ስር ተመ.

ቅራት ዝ.ክ.

ቅራና ስ 1. የቀርቀብ ጠፍር። 2. ለምራን፥ ለቀርቀብ ወይም ለመጫኛ የሚሆን ጠፍር ሊወጣው የሚችል የተሰፋና ገና በጠፍር መልክ ያልተሸነሸነ የበሬ ቆዳ።

ቅራኔ "***ቀረነ**" ስር ተመ.

ቅራፊ "***ቀረፈ**" ስር ተመ.

ቅሬ[1] ስ በሽርሙጥና የምትተዳደር ሴት።

ቅሬ[2] ስ የ"**እድር**" ን አንደኛ ፍቺ ተመ.

ቅሬታ "**ቀረ**" ስር ተመ.

ቅር

ቅሬታ (**ቅርታ**) ስ 1. ያለመስማማት፥ ያለመደሰት ስሜት።

ቅሬታ ተሰማው ቅር ተሰኘ።

ቅር ተሰኘ 1. ያለመርካት፥ ያለመደሰት ስሜት ተሰማው። 2. ተቀየመ። 3. አዘነ፤ ተከፋ።

ቅር አለው 1. ሳይረካ፤ የልቡ ሳይደርስ፥ ደስ ሳይለው ቀረ፤ ቅሬታ ተሰማው። 2. የተሟላ ለመሆን ትንሽ ተጨማሪ አስፈለገው። *ሰፌሩ ቅር አለው።*

ቅር ቅር አለው ከመለየት፤ ከመራራቅ ወይም የለመደውን ከማጣት ወይም ከአንዳች ነገር መጓደል የተነሳ ቅሬታ አደረበት፤ የመናፈቅ ስሜት ተሰማው፤ አንድ ነገር ትዝ አለው።

ቅር አሰኘ 1. አሳዘነ፤ አስቀየመ። 2. ቅሬታ አስከተለ።

ቅርምት "***ቀረመተ**" ስር ተመ.

ቅርስ ስ 1. የተካበተ ሃብት፤ ጥሪት። 2. እንደ ሃውልት፤ ህንፃ፤ የእደጥበብ ውጤቶች፥... የመሳሰለ የአንድን ሃገር ጥንታዊ ታሪክና ባህል የሚያንፀባርቅ፥ ከትውልድ ወደ ትውልድ የተላለፈና የሚተላለፍ ቋሚ መረጃ።

ቅርሻታም "**ቀረሸ**" ስር ተመ.

ቅርሻት ዝ.ክ.

ቅርሾ "**ቁርሾ**" ን ተመ.

ቅርቃር "**ቀረቀረ**" ስር "**መቀራቀር**" ን ተመ.

ቅርቃብ "**ቀረቀበ**" ስር "**ቀርቃባ**" ን ተመ.

ቅርቅፍት ስ ለመሄድ አመቺ ያልሆነ፤ በደንብ ያልቀና፤ ድንጋያማ፤ ወጣ ገባ መንገድ።

ቅርበት "**ቀረበ**" ስር ተመ.

ቅርብ ዝ.ክ.

ቅርታ "**ቅር**" ስር "**ቅሬታ**" ን ተመ.

ቅርናታም "**ቀረና**" ስር ተመ.

ቅርናት ዝ.ክ.

ቅርንጥስ ስ የተጣጣፈ አርጌ ወርቅ፤ ጭርንቁስ፤ ደባደቦ።

ቅርንጫፍ ስ 1. በዛፍ ወይም በማንኛውም እፅዋት ግንድ ዙሪያ ከታች እስከ አናት ድረስ ጋደም ጋደም እያለ የሚበቅል፥ የዛፍ ወይም የእፅዋት ክንፍ። 2. የአንድ ዋና አካል ቅጥያ፥ ዘርፍ።

ቅርንጫፍ መስሪያ ቤት ስ ከዋናው መስሪያ ቤት ራቅ ብሎ ሌላ ቦታ ላይ የሚገኝና ዋናው መስሪያ ቤት የሚያከናውነውን ተመሳሳይ ስራ የሚያከናውን የዋናው መስሪያ ቤት አካል፤ ዘርፍ።

ቅርንፉድ (ቁርንፉድ) ስ ጥሩ ሽታና ጣእም ያለው የቅመም አይነት።

ቅርጫ "ቀረጠ" ስር ተመ.

ቅርጫት ስ ከሸንበቆ፥ ከቀርከሃ፥ ከሃረግ፥... የሚበጅ ለእቃ መያዣና ማጓጓዣ የሚያገለግል የቤት እቃ።

ቅርጫት ኳስ ስ አምስት አምስት ተጫዋቾችን በያዙ ሁለት ቡድኖች መካከል፥ ከመሬት አስር ጫማ ያህል ከፍታ ባለው ምሰሶ ላይ በተሰቀለ የተቃራኒ ቡድን ቅርጫት ውስጥ ኳሱን በእጅ እየወረወሩ ለማስገባት የሚካሄድ የውድድር ጨዋታ አይነት፤ ኳሱም ቅርጫት ኳስ ይባላል(ስእሉን ኳስ ስር ተመ.) ።

ቅርፃ ቅርፅ "ቀረፀ" ስር ተመ.

ቅርፅ ዝ.ከ.

ቅርፊት "ቀረፈ" ስር ተመ.

ቅርፍርፍ ዝ.ከ.

ቅስም ስ አካላዊ ገፅታ፥ ወዘና፤ ብርታት፥ ጥንካሬ።

ቅስሙ ተሰበረ 1. ተስፋ በመቁረጥ ህሊናዊ ክብሩ፥ ጥንካሬው ወደቀ፤ ስሜቱ ተጎዳ። 2. አካላዊ ጥንካሬው፥ ወዘናው ጉዳት ላይ ወደቀ።

ቅስር "ቀሰረ" ስር ተመ.

ቅስቀሳ "ቀሰቀሰ" ስር ተመ.

ቅስቃሴ "*ቀሰቀሰ" ስር ተመ.

ቅስና "ቀሰሰ^{1}" ስር ተመ.

ቅስፈት "ቀሰፈ" ስር ተመ.

ቅሽምድምድ "ቀሸመደ" ስር ተመ.

ቅሽር "ቀሸረ" ስር **"ቀሸር"**ን ተመ.

ቅቅል "ቀቀለ" ስር ተመ.

ቅቅታም "ቀቀተ" ስር ተመ.

ቅቅት ዝ.ከ.

ቅበላ "*ቀበለ" ስር ተመ.

ቅቡጭ

ቅቡጭ አለ ግ እንስ፤ ጉድል አለ፤ በቶሎ፥ በድንገት እልቅ አለ።

ቅባት "ቀባ" ስር ተመ.

ቅቤ ዝ.ከ.

ቅብ ዝ.ከ.

ቅብቃብ "ቀበቀበ^{2}" ስር ተመ.

ቅብቅብ "ቀበቀበ^{1}" ስር ተመ.

ቅብቅቦ ስ ሳይጠበስ የሚበላ፥ በጨው የታሸ የማሽላ እሸት።

ቅብብል "*ቀበለ" ስር ተመ.

ቅብብሎሽ ዝ.ከ.

ቅብትት "ቀበተተ" ስር ተመ.

ቅብአ መንግስት "ቀባ" ስር ተመ.

ቅብአ ቅዱስ ዝ.ከ.

ቅብአ ኑግ ዝ.ከ.

ቅብአ ክህነት ዝ.ከ.

ቅብዝብዝ "ቃበዘ" ስር ተመ.

ቅብድድ "ቀበደደ" ስር ተመ.

ቅብጠት "ቀበጠ" ስር ተመ.

ቅብጥብጥ ዝ.ከ.

ቅትር "ቀተረ^{1}" ስር ተመ.

ቅትርት "ቀተረ^{2}" ስር ተመ.

ቅናሽ "ቀነሰ" ስር ተመ.

ቅናተኛ "ቀና^{1}" ስር ተመ.

ቅናት^{1} ዝ.ከ.

ቅናት^{2} "ቀና^{2}" ስር ተመ.

ቅናት^{3} "*ቀነተ" ስር ተመ.

ቅኔ "*ቀኘ" ስር ተመ.

ቅን "ቀና^{2}" ስር ተመ.

ቅንስናሽ "ቀነሰ" ስር ተመ.

ቅንቀና "ቀነቀነ^{2}" ስር ተመ.

ቅንቅናም "ቀነቀነ^{1}" ስር ተመ.

ቅንቅን ዝ.ከ.

ቅንቡርስ (ቅምቡርስ) ስ እርጥበት ባለው ኮሲ መሬት ወይም ተቆልሎ በከረመ አዛባ ውስጥ የሚገኝ ወፈር ያለ ነጭ ትል።

ቅንብር "*ቀነበረ" ስር ተመ.

ቅንብብ "ቀነበበ" ስር ተመ.

ቅንብቻ (ቅምብቻ) ስ ከስንደዶ ስፌት ወይም ከቆዳ የሚዘጋጅ የከተት ማስቀመጫ፤ መከተቻ።

ቅንብቻ ሆድ ጉስር ያለች ትንሽ ቦርጭ ያለው (ሰው)።

ቅንቦ(ቅምቦ) ስ ትላልቅ ፍሬ ያለው፥ ቅጠሉ ሰፋፊ የሆነና በበረሃ የሚገኝ የእፅዋት አይነት።

ቅንዛፌ "ቀነዘፈ" ስር ተመ.

ቅንዝረኛ "ቀነዘረ" ስር ተመ.

ቅንዝር ዝ.ከ

ቅንዝንዝ "*ቀነዘነዘ" ስር ተመ.

ቅንዳሽም "ቀነደሸ" ስር ተመ.

ቅንድል "ቀነደለ" ስር ተመ.

ቅንድብ "ቀነደበ^{1}" ስር ተመ.

ቅንጅት "*ቀነጀ" ስር ተመ.

ቅንጡ "ቀነጣ" ስር ተመ.

ቅንጣቢ "ቀነጠበ" ስር ተመ.

ቅንጣት ስ 1. ነጠላ፤ አንድ ብቻ የሆነ:: 2.ትንሽ::

ቅንጥ ስ በአይንና በጆሮ መካከል አካባቢ ላይ የሚገኝ አካል(ሰለሉን ሰውነት ስር ተመ.)::

ቅንጦተኛ "ቀነጣ" ስር ተመ.

ቅንጦት ዝ.ከ.

ቅንጯቢ "ቀነጨበ" ስር ተመ.

ቅንጬ ስ ከስንዴ ወይም ከገብስ ወይም ከአጃ ክክ የሚዘጋጅ የምግብ አይነት::

ቅንጭር "ቀነጨረ" ስር "ቀንጫራ" ን ተመ.

ቅንጭብ ስ ሲቆረጥ ወተት የሚመስል ፈሳሽ የሚወጣው በቆላና በወይና ደጋ የሚበቅል የእፅዋት አይነት::

ቅንፋት "ቀነፈ" ስር ተመ.

ቅንፍ ዝ.ከ$_{2}$

ቅኝ "ቀና^{2}" ስር ተመ.

ቅኝት$^{1}_{2}$ "ቃኘ^{1}" ስር ተመ.

ቅኝት^{2} "ቃኘ^{2}" ስር ተመ.

ቅዋሜ "*ቀወመ" ስር ተመ.

ቅው

ቅው አለ ግ የመጋጨት፡ ኳ የማለት ድምፅ ሰጠ ወይም አሰማ::

ቅው ቅው አለ ዝ.ከ.

ቅው ቅው አደረገ ግ የማጋጨት፣ የማንኳኳት፣ የመቀጥቀጥ ድምፅ አሰማ::

ቅዘናም "ቀዘነ" ስር ተመ.

ቅዘን ዝ.ከ.

ቅዛዛ ስ የብርሌ፣ የብርጭቆ፣... መስታወት ወይም ሰሊዳው::

ቅዝምዝም "*ቀዘመዘመ" ስር ተመ.

ቅዝቃዜ "ቀዘቀዘ" ስር ተመ.

ቅዝዝ አለው "ቀዘዘ" ስር ተመ.

ቅዥታም "ቃዠ" ስር ተመ.

ቅዥት ዝ.ከ.

ቅያሜ "*ቀየመ" ስር ተመ.

ቅያሬ (ቅያሪ) "ቀየረ" ስር ተመ.

ቅያስ "ቀየሰ" ስር ተመ.

ቅይድ "ቀየደ" ስር ተመ.

ቅይጥ "ቀየጠ" ስር ተመ.

ቅደም ተከተል "ቀደመ" ስር ተመ.

ቅዱሳት "ቀደሰ" ስር "ቅዱስ" ን ተመ.

ቅዱሳን ዝ.ከ.

ቅዱስ "ቀደሰ" ስር ተመ.

ቅዳሜ ስ በአርብና በእሁድ መካከል ያለው ቀን ስም፤ ከእሁድ ጀምሮ ሲቆጠር የሳምንቱ ሰባተኛ ወይም መጨረሻ ቀን፤ ቀዳሚትም ይባላል::

ቅዳም ሹር (ስኡር) ስ በስቅለት ማግስት የሚውለው ቅዳሜ ስም::

ቅዳሴ "ቀደሰ" ስር ተመ.

ቅዳጅ "ቀደደ" ስር ተመ.

ቅድ ዝ.ከ.

ቅድ "ቀዳ" ስር ተመ.

ቅድመአያት "ቀደመ" ስር ተመ.

ቅድሚያ ዝ.ከ.

ቅድም ዝ.ከ.

ቅድስት$^{1}_{2}$ "ቀደሰ" ስር "ቅዱስ" ን ተመ.

ቅድስት^{2} ስ በኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን በተለይ ክብ ቅርፅ ይዘው በተሰሩት ህንፃዎች ውስጥ በመቅደሱና በቅኔ ማህሌቱ መካከል ያለው ቦታ::

ቅድስና "ቀደሰ" ስር ተመ.

ቅጅ "ቀዳ" ስር ተመ.

ቅጠል ስ 1. ከግንዱ ላይ ለምለም ሆኖ የሚበቅል፣ ብዙውን ጊዜ ቀለሙ አረንጓዴ፣ አካሉ ስስ የሆነ የእፅዋት አካል ክፍል :: 2. ነጠላ፤ አንድ ብቻ (ለወረቀት)::

ቅጠላ ቅጠል ስ 1. አይነቱ የተለያየ ብዙ ቅጠል:: 2. እንደ ጎመን፣ ሰላጣ ላሉና ለሚበሉ የተክል አይነቶች የጥቅል መጠሪያ::

ቅጠል በጣሽ ስ (የን.አነ.) ቅጠላ ቅጠሎችን እየሰበሰበ በመቀመም የባህል መድሃኒት የሚያዘጋጅ (ሰው)::

ቅጠል የለሽ ለዛ ቢስ፤ ንግግሩ ጣእም የሌለው::

ቅጠልማ ቅ ቀለሙ ቅጠል የሚመስል፤ አረንጓዴ::

ቅጠልያ ዝ.ከ.

ቅጣተኛ "**ቀጣ**" ስር ተመ.

ቅጣት ዝ.ክ.

ቅጣጥይ (ቀጣጥይ) ስ በመጨረሻ የሚወጣ መንጋጋ።

ቅጥ ስ ስርአት፣ ደንብ።

ቅጡ ጠፋው 1.የሚያደርገውን አጣ፤ ተደናገረው። 2. ስርአት አጣ።

በቅጥ(በቅጡ) በደንብ፣ በስነስርአት፤ በትክክል።

አለቅጥ (ያለ ቅጥ) ከመጠን በላይ።

ቅጥ የለሽ የተበላሸ፣ ስርአት ያጣ።

ቅጥል "**ቀጠለ**" ስር ተመ.

ቅጥልጥል ዝ.ክ.

ቅጥረኛ "**ቀጠረ**" ስር ተመ.

ቅጥራን ስ 1. መጣብቅ ወይም ሙጫነት ያለው ዝፍት። 2. ሬንጅ፣ ካትራሜ።

ቅጥር^{1} "**ቀጠረ**^{1}" ስር ተመ.

ቅጥር^{2} "**ቀጠረ**^{3}" ስር ተመ.

ቅጥር ግቢ ዝ.ክ.

ቅጥቃጤ "**ቀጠቀጠ**" ስር ተመ.

ቅጥቃጭ "**ቀጠቀጠ**" ስር "**እንቅጥቃጭ**" ን ተመ.

ቅጥቅጥ "**ቀጠቀጠ**" ስር ተመ.

ቅጥበት "**ቀጠበ**" ስር ተመ.

ቅጥብ ዝ.ክ.

ቅጥይ(ቅጥያ) "**ቀጠለ**" ስር ተመ.

ቅጥጥብ "**ቀጠበ**" ስር ተመ.

ቅጥፈት "**ቀጠፈ**^{2}" ስር ተመ.

ቅጫማም "**ቀጨመ**" ስር ተመ.

ቅጫም ዝ.ክ.

ቅጭት "**ቀጨ**^{1}" ስር ተመ.

ቅፀላ "**ቀፀለ**" ስር ተመ.

ቅፅ ስ ጥራዝ፣ ተከታታይነት ያለውና በተለያየ ጥራዝ የተዘጋጀ መፅሃፍ።

ቅፅል ስ 1. (ሰዋ.) ከስምንቱ የንግግር ክፍሎች የአንደኛው ስም። 2. የአንድን ነገር ጠባይ ወይም መልክ ወይም መጠን፣... ለማሳየት የሚያገለግል ቃል (ለምሳሌ *ደግ ሰው*፣ *ቀይ ልጅ* ፣ *ጥቂት ገንዘብ* በሚለው ውስጥ "*ደግ*"፣ "*ቀይ*"፣ "*ጥቂት*" ቅፅል ናቸው)።

የቅፅል ስም ስ ከግብሩ ወይም ከባህርዩ ወይም ከመልኩ፣... የተነሳ በዋናው መጠሪያ ስም ላይ እንደ ተጨማሪ ሆኖ የሚያገለግል ስም።

ቅፅረ ግቢ "**ቀጠረ**^{3}" ስር "**ቅጥር ግቢ**" ን ተመ.

ቅፅር "**ቀጠረ**^{3}" ስር **ቅጥር**" ን ተመ.

ቅፅበት ስ አፍታ፣ በጣም አጭር የሆነ የጊዜ ልክ።

ቅፅበተ አይን ስ አይን እንደ መክደን ብሎ-እስኪገለጥ ድረስ ያለና እጅግ በጣም አጭር የሆነ የጊዜ ልክ።

በቅፅበት (ከመቅፅበት) ተው.ግ. እጅግ በጣም አጭር በሆነ ጊዜ ውስጥ፣ ወዲያውኑ።

ቅፈፍ "**ቀፈፈ**^{1}" ስር ተመ.

ቅፍለት ስ አንዱ ከሌላው ኋላ በመሆን እንደሰንሰለት ተቀጣጥሎ የሚጓዝ የተጫነ የነጋዴ ግመል መንጋ።

ቅፍንድ "**ቀፈተ**" ን ተመ.

ቅፍድድ (ቅፍድ) "**ቀፈደደ**" ስር ተመ.

ቆ የ "**ቀ**" ፊደል ሳብእ ዘር።

ቆለለ ግ 1. ከመረ፣ አነባበረ፣ አደራረበ፤ በአንድ ላይ ሰበሰበ። 2. አበዛ፤ ጨመረ፣ ከመጠን በላይ ከፍ አደረገ (ዋጋን፣...)።

ቁልል ቅ ክምር።

ቁልልታ ስ ጉብታ፣ ከአካባቢው ተለይቶ እንደ ኮረብታ ከፍታ ያለው መሬት።

ቆለመመ ግ ጠመዘዘ፣ ቀለሰ፣ አጎበጠ።

ቆልማማ ቅ 1. ጎባጣ፣ ቅልስ። 2.(ዘይ.) ጠማማ፣ ወልጋዳ (ለጠባይ)።

ተቆላመመ ግ 1. ተጠማዘዘ፣ ተጣመመ፣ ተወላገደ። 2. አልገጥም፣ አልስማማ አለ፣ አስቸገረ፣ እምቢ አለ።

አቆላመመ ግ አጠማዘዘ፣ አጎበጠ፣ አጣመመ።

***ቆለመጠ**

ቁልምጫ ስ የመውደድ፣ የመለማመጥ፣ የማባበል፣ የማሞካሸት፣ የማወደስ፣... አነጋገር ወይም አጠራር።

የቁልምጫ ስም ስ ዋናውን የመጠሪያ ስም ቅርፅ ለወጥ አድርጎ ለመጥራት የሚያገለግል፣ በቤተሰብ ወይም በጓደኛ አማካይነት የሚወጣ የፍቅር ስም። ለምሳሌ አበበን "አቤ"፣ ዘነበችን "ዘኑ" እንደማለት ያለ አጠራር።

ተቆላመጠ ግ በቁልምጫ ተጠራ፤ ተሞካሸ።

አቆላመጠ ግ በቁልምጫ ጠራ፤ አሞካሸ።

አቆላማጭ ቅ አሽቃባጭ።

ቆለቆለ ግ ወደታች ወረደ፣ ዝቅ አለ።

ቁልቁል ተው.ግ. ወደታች፣ ዝቅ ወዳለ ቦታ።

ቁልቁለት ስ ወደ ዝቅተኛ ቦታ የሚወስድ ተዳፋትነት ያለው መንገድ፣ ቦታ።

ቆልቋላ ቅ ተዳፋትነት ያለው፥ ዘቅዛቃ።

ተቆለቆለ ግ ቁልቁል ሄደ፥ ወደታች ወረደ።

ተሽቆለቆለ ዝ.ክ.

አቆለቆለ ግ 1. ከከፍተኛ ወደ ዝቅተኛ ቦታ ሄደ፥ አዘቀዘቀ፥ ወደታች ወረደ። 2. ቀነሰ፥ ዝቅ አለ፥ ወረደ (ዋጋ)።

አቆልቋይ ስ 1. ወደታች የሚሄድ፥ ወራጅ። 2. በአንድ ጊዜ ብዙ ሰው ሊመገብበት የሚችል ሞላላ ገበታ፤ አውራጅ፤ አቆልቋይ ገበታም ይባላል።

አሽቆለቆለ ግ 1. ወደታች ወረደ፥ ቁልቁል ሄደ። 2. ዝቅ አለ፥ ቀነሰ፥ ወረደ (ዋጋ)።

ቆለቆል ስ መርዛማ የሆነና ወተት የሚመስል ነጭ ፈሳሽ የሚወጣው፥ በቆላማ ቦታ የሚገኝ፥ ቁልቋል መሳይ የእፅዋት አይነት።

ቆለኛ "**ቆላ**²" ስር ተመ.

ቆለጥ ስ ከወንዴ ብልት መባቀያ ስር ከረጢት መሰል በሆነ የአካል ክፍል ውስጥ የሚገኝ፥ ወንዴ ዘርን የሚያመነጭና ጥንድነት ያለው ፍሬ የሚመስል አካል።

ቆለጣም ቅ (ዘይ.) ትእቢተኛ ጎረምሳ።

***ቆለጨ**

ቆለጭ ቅ አይነ መልካም፥ አይነ ከብላላ።

ቁልጭ አለ ግ 1. ጠራ፥ ንፁህ ሆነ። 2.ወለል ብሎ፥ ግልፅ ሆኖ ታየ። 3. ደፍ ወጣ፥ ግልፅ ሆነ።

ቁልጭ ያለ ቅ 1. ያማረ፥ የጠራ፥ ንፁህ የሆነ። 2. ግልፅ የሆነ።

ቁልጭ አደረገ ግ 1. አጠራ፥ ንፁህ አደረገ። 2. ግልፅ አደረገ።

ቁልጭ ቁልጭ አለ ግ ከጭንቀት፥ ከጉጉት፥... የተነሳ አይኑን ወዲያና ወዲህ በማንከባለል አየ፥ ተመለከተ።

ቁልጭ ቁልጭ አደረገ ግ ከጭንቀት፥ ከጉጉት፥...የተነሳ አይኑን ወዲያና ወዲህ በማንከባለል አየ፥ ተመለከተ።

ቁልጭልጭ ቅ ውብ፥ መልካም፥ አይናማ።

ቁልጭልጭ አለ ግ ተዋበ፥ ፀዳ፥ አማረ።

ቁልጭልጭ አደረገ ግ አስዋበ፥ አፀዳ፥ አሳመረ።

ተቁለጨለጨ ግ 1. ከጭንቀት፥ ከጉጉት፥... የተነሳ አይኑ ወዲያና ወዲህ እየተንከባለለ አየ፥ ተመለከተ። 2. ተዋበ፥ አማረ።

አቁለጨለጨ ግ 1. ከጭንቀት፥ ከጉጉት፥... የተነሳ አይኑን ወዲያና ወዲህ እያንከባለለ አየ፥ ተመለከተ። 2. አስዋበ፥ አሳመረ። 3. አጓጓ፥ አስጎመጀ።

ቆለፈ ግ 1. በርን፥ ሳጥንን፥... በቁልፍ ዘጋ፥ እንዳይከፈት አደረገ። 2. የሸሚዝን፥ የኮትን፥ የቀሚስን፥ የኪስን፥...ክፍተት በአዝራር፥ በቻርኔላ(በዚፕ)፥... አያያዘ፥ ገጠመ፥ ዘጋ። 3. አጎበጠ፥ ቀለሰ። 4. አንቆ ያዘ፥ አልለቅ፥ አላንቀሳቅስ አለ።

ቁልፍ ስ 1. የበር፥ የሳጥን፥...መዝጊያ እንዳይከፈት አንቆ ወይም ጠርቅሞ የሚይዝ፥ ከብረታ ብረት የሚሰራ እቃ፥ ጓንጓቸር። 2. የቁልፍ መክፈቻ እና መቆለፊያ። 3. አዝራር። 4. (ዘይ.) ዋነኛ፥ ከፍተኛ ሚና መጫወት የሚችል ወይም የሚያስችል (ሰው፥ ቦታ፥...)። ቅ 5. በቁልፍ የተቆለፈ፥ የተዘጋ። *ቤቱ ቁልፍ በመሆኑ መግባት አልተቻለም።*



ቁልፍ

ቆላፋ ቅ ከወደጫፉ የተቀለበ፥ የተቆላመመ (እንጨት ወይም ብረት)።

ቁልፍ ቅ (ዘይ.) ዝግ፥ መናገር የማይችል።

ቆላለፈ ግ 1. አንዱን ከሌላው ጋር አጣላለፈ፥ አወሳሰበ፥ አያያዘ። 2. ቆለፈ።

ቁልፍልፍ ቅ አንዱ ከሌላው ጋር የተጠላለፈ፥ የተወሳሰበ፥ የተያያዘ።

መቆለፊያ ስ 1. ቁልፍ ወይም ጓንጓቸር። 2. የ"**ቁልፍ**"ን 2ኛ ፍቺ ተመ. 3. እንደ አዝራር ያለና በቁልፍነት የሚያገለግል ማንኛውም ነገር።

ተቆለፈ ግ 1. ተዘጋ፥ ተገጠመ። 2. ጎበጠ፥ ታጠፈ፥ ተቀለሰ።

ተቆላለፈ ግ 1. ተጠላለፈ፥ ተሳሰረ፥ ተወሳሰበ፥ ተያያዘ (አንዱ ከሌላው ጋር)። 2. አንድም ሳይቀር ሁሉም ተቆለፈ፥ ተዘጋ።

***ቆለፈ**

ቆለፈት ስ የወሸላ ሸፋን፥ ሸለፈት፥ ልምቡጥ።

ቆለፈታም ቅ (ስድብ) ሸለፈታም፥ ወሸላ፥ ያልተገረዘ (ወንድ)።

ቆላፍ ቅ 1. ያልተገረዘ፥ ወሸላ። 2. የአህዛብ ወገን፥ አረማዊ።

ቆላ¹ ግ 1. ምግብን እሳት ላይ አድርጎ

በማስማትና በላዩ ላይ እንደ ጥራጥሬ ያሉ የምግብ አይነቶችን በማስቀመጥና በማመስ አበሰለ። 2. ከሰማ ምጣድ ላይ የተደረገን ጥራጥሬ ወይም ሌላን ነገር በመቁያ አመሰ፤ አገላበጠ። 3. አቃጠለ፤ ፈጀ (በሽታ፤ ፀሃይ፤ ረሃብ፤ ችጋር፤ ጥይት፤...)። 4. አቃረ፤ አቃጠለ(ልብን)። 5. ወዘወዘ፤ ወነወነ፤ ነቀነቀ (ውሻ፤ ድመት፤... ጅራትን)።

ቆላሙ (ነውር) የወሲብ ፍላጎት አቅንዘነዘው።

መቁሊያ (መቁያ) ስ ከሰማ ምጣድ ላይ የተነሳን ጥራጥሬ፤ ቡና፤... እንዳያር እያመሱ ወይም እያገላበጡ ለማብሰል የሚረዳ ከጫፉ ቆልመም ያለ እንጨት ወይም ብረት...።

ቁሌት ስ እንደ ሽንኩርት፤ በርበሬ፤ ቅመም፤ ዘይት ያሉትን ከትንሽ ውሃ ጋር አንድነት አድርጎ በማብሰል የሚዘጋጅና በርከት ብሎ ለሚሰራው ወጥ እንደ መነሻ ሆኖ የሚያገለግል የወጥ ጅምር፤ ውጥን።

ቁሊታም ቅ (ነውር፤ ስድብ) ከፍተኛ የወሲብ ፍላጎት ያለው።

ቆሎ ስ ከሰማ ምጣድ ላይ ተደርጎና ታምሶ የበሰለ ጥራጥሬ።

የቆሎ ተማሪ ስ እየለመነ ከየመንደሩ የሚያገኘውን ቁራሽ እንጀራ፤ እንዲሁም ጥሬ ጥሬውን በቆሎ መልክ እያዘጋጀ በመመገብ እንደ ንባብ፤ ዜማ፤ ቅኔ፤... ያሉትን የትምህርት አይነቶች የሚቀስል የቤተክህነት ተማሪ።

ተቆላ ግ (ነውር) የወሲብ ፍላጎት ተነሳበት።

ተቁላላ ግ 1. ወጥ ለመስራት በቀዳሚነት የሚፈለገው ቅመም (ሽንኩርት፤ ቅባት፤ በርበሬ ወይም ማቁላሊያ) እሳት ላይ በተጣደ ድስት ውስጥ ተደርጎ እየተማሰለ ተቀቀለ፤ የወጡ የመጀመሪያ ደረጃ ስራ ተከናወነ። 2. (ዘይ.) ተጉላላ።

አቁላላ ግ ወጥ ለመስራት በቀዳሚነት የሚፈለገውን ቅመማቅመም ወይም ማቁላሊያ እሳት ላይ በተጣደ ድስት ውስጥ ጨምሮ እያማሰለ ቀቀለ፤ አበሰለ።

ማቁላሊያ ስ እንደ ኣብሽና በሶብላ፤... ያሉ ቅመሞች ተጨምረውበት የተዘጋጀ የሽንኩርት ዱቄት።

ቆላ^2 ስ አቀማመጡ በጣም ዝቅተኛና ሞቃታማ የሆነ ቦታ፤ ሃገር፤ የደጋ ተቃራኒ።

ቆላና ደጋ ረገጠ 1. ሲራመድ ሚዛኑን ስቶ እዚህና እዚያ ማዶ ረገጠ፤ ተግተረተረ። 2. ያልተስተካከለ ነገር በመናገር ዘባረቀ፤ ዘላበደ።

የቆላ ቁስል ስ እየጠቀጠቀ የሚያስቸግርና ቶሎ የማይድን የቁስል አይነት።

የቆላ ገንቢ ስ በጣም ቆላማ በሆነ አካባቢ የሚገኝ፤ ከብቶችን እየነደፈ የሚገድል መርዛማ የገንቢ አይነት።

ቆለኛ ቅ 1. በቆላ የሚኖር። 2. ሸክላ በመስራት ወይም ቆዳ በመፋቅ፤ በማልፋትና በማለስለስ ወይም ለተለያዩ አገልግሎት የሚውሉ ብረታብረቶችን በመስራት የሚተዳደር የእጅ ባለሙያ።

ቆላማ ቅ ቆላነት ያለው፤ ሞቃታማ።

ቆላለፈ "**ቆለፈ**" ስር ተመ.

ቆላፋ ዝ.ከ.

ቆላፍ፡ "***ቆለፈ**" ስር ተመ.

ቆሌ ስ የአንድን ሰው ወይም አካባቢ ደህንነት ይጠብቃል ወይም ግርማ ሞገስ ይሰጣል ተብሎ የሚታሰብ እንደ ውቃቢ፤ ዛር፤ ከራማ፤ አድባር፤... ያለ የባእድ እምልኮ መንፈስ።

ቆሊ ገፈፈ በጣም አስደነገጠ።

ቆሊው ተገፈፈ ውቃቢ ራቀው፤ ግርማ ሞገሱን አጣ፤ በጣም ደነገጠ።

ባለ ቆሊ ቅ ውቃቢ፤ ዛር ያለበት (ሰው)።

ቆሊቢስ ቅ 1. ግርማ ሞገስ የሌለው፤ ጥላ ቢስ፤ ከውካዋ። 2. ረድኤት የለሽ።

ቆልማሚት ስ በጣም ረዥም ቅልጥምና ቆልማማ የሆነ ረዥም አንገት ያለው፤ በአብዛኛው መልኩ ነጭ የሆነ፤ ብዙውን ጊዜ በሃይቆች አካባቢ በመንጋ ሆኖ የሚገኝ የአሞራ አይነት(ስእሉን አሞራ ስር ተመ.)።

ቆልማማ "**ቆለመመ**" ስር ተመ.

ቆልቋላ "**ቆለቆለ**" ስር ተመ.

ቆሎ "**ቆላ^1**" ስር ተመ.

ቆመ ግ 1. ከተቀመጠበት ተነሳ፤ ብድግ አለ። 2. ተገተረ። 3. ተገታ፤ ታገደ። 4. እንቅስቃሴው፤ ሂደቱ ተቋረጠ፤ መስራቱን ተወ። *ሰአቱ ቆመ።* 5. አበቃ፤ አለቀ፤ ተፈፀመ። *ንግግሩ እንደቆመ ትርኢቱ ይቀጥላል።* 6. ጠበቃ፤ ወኪል፤ ኢጋች ሆኖ ተከራከረ። *ለሰላም እንቆማለን።* 7. ረገጠ። *እግሩ ላይ ቆመ።* 8. ተሰራ፤ ተቋቋመ፤ ተመሰረተ፤ ተተከለ። *ትምህርት ቤት ቆመ/ ሃውልት ቆመ።*

ቆሚ ቀረች ባል ሳታገባ ቀረች።

ቆሞ ቀር (ቁሞ ቀር) ቅ (ስድብ) ባል ሳታገባ ጊዜው ያለፈባት።

መቆሚያ ቅ መጨረሻ፤ ማለቂያ። *ወሬው መቆሚያ የለውም።*

መቋሚያ ስ ብዙውን ጊዜ ካህናት በቤተክርስቲያን ውስጥ



መቋሚያ

የሚደገፉበት፥ ዝማሜ የሚዘሙበት፥ የሚመረኮዙትና በስተ ላናቱ በኩል ለመደገፊያነት እንዲመች ሆኖ የተሰራ ምርኩዝ።

በቁሙ (በቁም) ተው.ግ. 1. በህይወት እያለ። 2. ሳይቀመጥ፡ እንደቆመ፡ ሳያርፍ። 3. ሳይንቀል፡ ሳይታጨድ፡ ሳይሰበሰብ፥ ሳይወቃ፡ በተዘራበት እርሻ ላይ እንዳለ፡ *ሰብሉን በቁሙ ሸጠው።*

በቁሙ ሞተ 1. መጥፎ፥ አሳዛኝ ነገር ደረሰበት ወይም ተፈፀመበት። 2. በጣም ተጎሳቆለ፡ ከሰውነት ተራ ወጣ።

በቁሙ የሞተ ቅ እርባና የሌለው፡ ራሱን ያዋረደ፡ መንፈሰ ደካማ።

ቁም ለቁም (ስድብ) 1. ቀውላላ፡ ረዥም፡ ከርፋፋ። 2. ስራ መስራት የማትወድ፡ ገልቱ፡ ሰነፍ። 3. በመርዱ ወይም በጎኑ ሳይሆን በቁመቱ።

ቁምሳጥን ስ ቁመቱ ረዘም ያለና የቤት በር የመሰለ መዝጊያ ያለው፡ ብዙውን ጊዜ ለልብስ መስቀያና ማስቀመጫ የሚያገለግል ትልቅ ሳጥን።

ቁም ስቃይ ተው.ግ. ከባድ ያለ ስቃይ፡ ጭንቅ፥ መከራ።

ቁም ስቅሉን አየ መከራ ተቀበለ፥ተሰቃየ።

ቁም ነገር ስ ፍሬ ያለው ወይም ጠቃሚ የሆነ ነገር፥ ሃሳብ።

ቁም ንባብ ስ በቤተክህነት የንባብ ትምህርት ቤት ከውርድ ንባብ ቀጥሎ የሚሰጥ ፈጠን ያለ የአነባበብ አይነት።

[የ] ቁም እስር ስ ከተወሰነ የቦታ፥ የሃገር ክልል ወይም አካባቢ ውጭ መንቀሳቀስ የማይፈቀድበት የእስር አይነት፤ ግዞት።

ቁም ከብት ስ እንደ በግ፥ ፍየል፡ በሬ፡ ላም፡... ያለ የቤት እንስሳ ሃብት።

ቁም ዜማ ስ (ቤ.ክህ.) የድጓ ዜማ።

ቁም ፅህፈት ስ ብዙውን ጊዜ በመቃ ብእር በብራና ላይ የሚፃፍ ጉልህና ውብ የሆነ የእጅ ፅሁፍ።

ቁመት ስ 1. የርዝመት መጠን። 2. ከእግር እስከ አናት ድረስ ያለው ርዝመት።

ቁመና ስ የሰውነት ወይም የአካል ቅርፅ፥ አቋም።

በቁመና 1. በህይወት እያሉ። 2. በአካል ቅርፅ፡ በአቋም። 3. ሳይሰበሰብ በተዘራበት እርሻ ላይ እንዳለ። *ሰብሉን በቁመናው ሸጠው።*

ቋሚ ስ 1. ከእንጨት በሚሰራ የቤት ግድግዳ ዙሪያ እልፍ እልፍ የሚተከል ቀጥ ያለ ጠንካራ እንጨት።ቅ 2. ኣሳሳፊ፥ አስተናጋጅ፡ አስተናባሪ። 3. በህይወት ያለ (የሟች ዘመድ፥ ቤተሰብ፥ ወገን)። 4. ዘላቂ።

ቋሚ ሰራተኛ ስ የሙከራ ጊዜውን የጨረሰና መደበኛ ተቀጣሪ የሆነ ሰራተኛ።

ተቆመ ግ (ቤ.ክህ.) በዜማ ተባለ፡ ተፀለየ። *ሰዓታት ተቆመ።*

ተቋም ስ ልዩ ምርምርና ጥናት የሚካሄድበት፡ የልዩ ልዩ ሙያዎች ስልጠና የሚሰጥበት ድርጅት።

ተቋቋመ ግ 1. ተመሰረተ። 2. ስር ሰደደ፡ ተጠናከረ፥ ደረጀ። *እስኪቋቋሙ ድረስ ኑሮ ያስቸግራል።* 3. መከተ፥ ተከላከለ። 4. ተሟገተ፡ ተከራከረ።

መቋቋሚያ ስ አንድን ተግባር ለማካሄድ የሚያስፈልግ ገንዘብ ወይም ሌላ ንብረት፤ መነሻ ሃብት።

አቆመ ግ 1.ብዙ እንዲቆም፡ እንዲቆይ አደረገ፥ አስቆመ። 2. ብድግ፡ ቀጥ አደረገ። 3. ገታ፥ አገደ፥ ከለከለ፡ አስቀረ። 4. ገተረ። 5. እንዳይሰራ፡ እንዳይንቀሳቀስ አደረገ። 6. የመሄድ፥ የመምጣት፥ የመጓጓዝ እንቅስቃሴ አቋረጠ። 7. መሰረተ፡ አቋቋመ። 8. አዘቀ፥ ፈፀመ።

አቋም ስ 1. ማንኛውም ነገር ከእድሜ፡ ከጥንካሬ፥...አኳያ ሲገመገም የሚገኝበት ሁኔታ፡ አኳሁን። 2. አንድን ጉዳይ አስመልክቶ የሚወሰድ የራስ አስተያየት፡ አመለካከት፥ ፍላጎት፥ ውሳኔ።

የአቋም መግለጫ ስ አንድን ጉዳይ አስመልክቶ በተደረገ ስብሰባ ላይ የተላለፉ የውሳኔ ነጥቦችን ይዞ የሚወጣ መግለጫ።

አቋም ወሰደ አንድን ጉዳይ በተመለከተ አንድ አይነት አመለካከት፥ ውሳኔ ያዘ።

አቋቋመ ግ 1. መሰረተ፥ ሰራ፡ አበጀ። 2.አደራጀ፡ አጠናከረ፥ አበረታታ፡ አገዘ፥ ረዳ። *ልጆቴ ንግድ ቤት ከፍታ እንድትሰራ ያቋቋሟት ወላጆቿ ናቸው።* 3. ወላጆች ልጃቸውን ክርስትና በሚያስነሱበት ቦታ በመገኘት ሥነሥር ሰርአቱን አከበረ፡ ተከታተለ።

አቋቋም ስ 1. የመቆም ሁኔታ (ቀጥ በማለት ወይም ባለማለት)። 2. መዘምራን ከመቋሚያ ውዝዋዜ፥ ከፀናፅልና ከከበሮ ድምፅ ጋር እያቀናጁና እያስማሙ የሚያዜሙት የማህሌት ዜማ፤ ትምህርቱም አቋቋም ይባላል።

አስቆመ ግ 1. ብዙ አስጠበቀ (በመንገድ ላይ)። 2. አሳገደ፡ አስከለከለ። 3. እንዲያቆም ወይም እንዲቆም አደረገ።

ቆመረ ግ ቁማር ተጫወተ።

ቁማር ስ ገንዘብን፥ ንብረትን አሲዞ በጨዋታ ብልጫ ተከክሮ አንዱ ሌላውን ለመርታትና የተያዘውን ለመውሰድ ወይም ለመብላት የሚደረግ ጨዋታ።

ቁማርተኛ ስ አዘውትሮ ቁማር የሚጫወት ሰው።

ቆመጠ ግ 1. ቆማጣ አደረገ፥ አካልን አጎደለ (ቁምጥና ወይም ደዌ ስጋ)። 2. ጎመደ፥ ጎረደ፥ ቢበሰ፡ ቆረጠ። 3. በዱላ መታ፡ ነረተ። 4. (ዘይ.) አሳነሰ፥ ቀነሰ፡ አጎደለ። *ወፍጮው እህሉን ቆምጦ አስቀረው።*

ቆምጦ ቀጥል ቅ ውሽታም፡ ያልሆነውን ሆነ፥ ያልተደረገውን ተደረገ ብሎ የሚያወራ።

ቁምጣ ስ 1. ከጉልበት በላይ የሚውል አጭር ሱሪ። 2. የኩንታል አጋማሽ የሚሆን ጆንያ።

ቁምጥና ስ ሙላ ሰውነትን የሚያቆስል፡ የሚቆራርጥ ደዌ ስጋ።

ቆመጥ ስ አጭርና ወፈር ያለ ዱላ።

ቆማጣ ቅ (ስድብ) በደዌ ስጋ አካሉ የቆሰለ፥ የተቆረጠ፥ የተጎዳ (ሰው)። 2. አጭር፥ ሰንካላ፡ ጎደሎ።

ቁምጥ አለ ግ 1. ተቆመጠ። 2. እሁሰት ተከፈለ፥ ግምስ አለ። 3. (ዘይ.) ሳይታሰብ በድንገት መጠኑ አነሰ፥ ቀነሰ።

ቆማመጠ ግ 1. ብዙ ቦታ ላይ ቆመጠ፥ አቆሰለ (ደዌ ስጋ)። 2. ቆራረጠ፥ ጎራረደ።

ቁምጥምጥ (ቆመጥማጣ) ቅ (ስድብ) ቆማጣ።

ቁምጥምጥ አለ ግ ተቆማመጠ።

ቁምጥማጭ ቅ ቁርጥራጭ።

ተቆመጠ ግ 1. ደዌ ስጋ (ቁምጥና) ያዘው፥ ቆሰለ፡ ቆማጣ ሆነ። 2. ተቆረጠ፥ ተጎመደ።

ተቆማመጠ ግ 1. በቁምጥና ህመም ቆሳሰለ፡ አካሉ በቁስል ተበጣጠሰ። 2. ተቆራረጠ፥ ተጎማመደ።

ቆሞስ ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ)ስልጣነ ክህነቱ ከኤጲስቆጶስ በታች የሆነ የቤተክርስቲያን መንፈሳዊ አባት።

ቆረመ ግ ጭንቅላትን በትንሹ መታ፥ ለኮፍ አደረገ፥ ኮረኮመ።

***ቆረመደ**

ቆርማዳ (ቆረመድ) ቅ የተጎሳቆለ፡ ጨብጣ፥ ድህነት ያጠቃው።

ተቆራመደ ግ 1. ተኮማተረ፥ ተኮራመተ፡ ተጨበጠ፥ ቆረፈደ። 2. በችግር፡ በድህነት ተጎሳቆለ፥ ተሰቃየ።

ተቆረማመደ ግ ተቆራመደ።

አቆራመደ ግ 1. አኮማተረ፡ አኮራመተ፥ አቆረፈደ። 2. በችግር ፡ በድህነት አጎሳቆለ፡ አሰቃየ።

አቆረማመደ ግ አቆራመደ።

ቆረረ^{1} ግ በቀጭኑ ክለል ብሎ ወረደ፡ ፈሰሰ (ፈሳሽ)።

ቁርር ብሎ ወረደ ግ ቆረረ።

መቁረርት ስ ብዙውን ጊዜ በቤተክርስቲያን ውስጥ የቅዳሴ ዐበል የሚያድሱበት እንደማንቆርቆሪያ ያለ እቃ፡ ኩስኩስት።

ቆረረ^{2} ግ እጅግ በጣም በረደ፥ ቀዘቀዘ።

ቁር(ቆራ) ስ እጅግ በጣም ሃይለኛ የሆነ ቅዝቃዜ፥ ውርጭ።

ቆረሰ ግ ገመሰ፡ ከፈለ፥ ቀረደደ፡ ሸረፈ (እንጀራን፡ ዳቦን፥...)።

ቁራሽ ቅ 1. የእንጀራ ክፋይ ወይም ሽራፊ። 2. ትንሽ። *ቁራሽ መሬት አለችኝ።*

ቁርስ ስ ብዙውን ጊዜ ጠዋት የሚበላ መጠነኛ ምግብ።

ቁርስራሽ ቅ ብዙ ቁራሽ፡ ሽርፍራፊ።

ተቆረሰ ግ ተገመሰ፡ *ተከፈለ፥ ተቀረደደ፥* ተሸረፈ (እንጀራ፥ ዳቦ፥...)።

ተቋረሰ ግ ተካፈለ፡ ተጋራ (ምግብን)።

አቋረሰ ግ አካፈለ፥ አጋራ፡ አሳተፈ (ምግብን)።

***ቆረሰሰ**

ቆርሳሳ(ቆረሰስ) ቅ ከርፋፋ፥ ዘገምተኛ፥ ቀርፋፋ።

ተንቆረሰሰ ግ ቀስ እያለ ተራመደ፡ አዘገመ፡ ተንቀረደደ።

አንቆረሰሰ ግ በቀስታ አራመደ፡ አስኬደ፡ አንቀረደደ።

ቆረቆረ ግ 1. ወጋ፥ ጎረበጠ፡ አሳመመ፡ ምቾት ነሳ (አይንን፡ ገላን)። 2. መታ፥ አንኳኳ (በርን፥ ጠረጴዛን፥...)። 3. ቆጨ፡ ቅር አሰኘ፥ አሳዘነ፥ ከነከነ (ነገር፥ ድርጊት፥ ሁኔታ)። 4. ጀመረ፡ መሰረተ፡ ሰራ (መንደርን፥ ከተማን)። 5. በመቆርቆሪያ እየታገዘ የሸክላን ቀዳዳ በሞራና በጨርቅ ጠቀጠቀ፥ ደፈነ፥ ቀዳዳው እንዳያፈስ መረገ። 6. በሹል ብረት ወይም በመቆርቆሪያ በሳ፥ ነደለ፡ ሸነቆረ። 7. በትካዜ መንፈስ መሬትን መታ መታ አደረገ፡ ጫረ።

መቆርቆሪያ ስ 1. የብረት፡ የቆርቆሮ፡... ሙብሻ፡ መሸንቆሪያ፥ እንዲሁም የተሸነቆረ ሸክላን በጨርቅና በሞራ እየጠቀጠቀ ለመድፈን የምታገለግል ሹል ብረት። 2. እንስተኛ መዶሻ።

ተቆረቆረ ግ 1. አዘነ፡ ቅር ተሰኘ፡ ተቆጨ። 2. ተጀመረ፥ ተመሰረተ፥ ተሰራ (መንደር፡ ከተማ)።

ተቆርቋሪ ቅ አሳቢ፡ አዛኝ፡ የሚቆጭ።

አይቆረቁሬ ክፋት፡ ተንኮል የማያውቅ፥ ጥሩ

ጠባይ ያለው፥ ሰው የማያስቀይም።

*ቆረቆረ

ተንቆረቆረ ግ 1. ፈሳሽ የሆነ ነገር በቀጭኑ ወረደ፥ ፈሰሰ። 2. ተቀዳ። *ጠጁ በጠርሙስ እየተንቆረቆረ ተቀምጧል።*

አንቆረቆረ ግ 1. ፈሳሽ የሆነን ነገር በቀጭኑ ቀዳ፥ ከአንዱ እቃ ወደ ሌላው እቃ አስተላለፈ። 2. ዘለግ ባለና በሚያስደስት ድምፅ አዜመ። *ዜማውን አንቆረቆረው።*

ማንቆርቆሪት ስ ፈሳሽነት ያለውን (እንደ ዘይት፣ ጋዝ፥...ያለን) ነገር ከአንዱ እቃ ወደ ሌላው ያለማፍሰስ በትክክል ለማዛወር ወይም ለመቅዳት የሚረዳ እንደ ቅል አንገት ጠበብ ያለ ቀዳዳ ወይም ጡት ያለው እቃ።

ማንቆርቆሪት

ማንቆርቆሪያ ስ ብዙውን ጊዜ ለጠላና ለጠጅ ማደያ የሚያገለግል፥ በውስጡ ያለውን ፈሳሽ ወደ ሌላ እቃ ውስጥ ያለማፍሰስ ለማዛወር የሚረዳ እንደ ጀበና ያለ ጡት ያለው፥ ከኒኬል ወይም ከሌላ ማእድን የሚሰራ የቤት እቃ።

ቆረቆር ስ ራስ ላይ ጉብ ጉብ ብሎ የሚወጣ የቁስል ህመም አይነት።

ቆረቆራም ቅ (ስድብ) ቆረቆር ያለበት።

ቆረቆሰ^1 ግ በገና ጨዋታ ጊዜ ጨዋታውን ጀመረ፥ ባረከ (እሩሩን በገና ዱላ በመምታት)።

ቁርቆሳ ስ ጅመራ (የገና ጨዋታ ወይም የጠብ)።

ተቆራቆሰ ግ 1. በገና ጨዋታ ላይ ዱላና ዱላን በማጋጨትና እሩርን በመምታት ጨዋታውን ጀመረ። 2. ተጋጨ፥ ተጣላ፤ ጠብ፥ ጦርነት ጀመረ፥ ተጫረ።

አቆራቆሰ ግ 1. የገና ጨዋታ ተጫዋቾች (የቡድን አባቶች) በግብ አማካይ ቦታ ላይ ሆነው እሩሯን እኩል ተሸምተው በመምታት ጨዋታውን እንዲጀምሩ አደረገ፤ እንደ ዳኛ ሆኖ የጨዋታውን አጀማመር ስርአት ተቆጣጠረ። 2. አጣላ፥ አጋጨ፥ እንዲተናከሱ፣ እንዲጣሉ አደረገ።

አቆራቋሽ ስ 1. የገና ጨዋታ ተጫዋቾችን የጨዋታ አጀማመር ስርአት የሚቆጣጠር ሽማግሌ፥ ዳኛ። 2. (ዘይ.) አንዱን ከሌላው ጋር የሚያጣላ፥ የሚያጋጭ፣ ነገረኛ (ሰው)።

ቆረቆሰ^2 ግ አረጀ፥ ተቆራመደ፣ ቆረቆዘ።

ቆርቋሳ ቅ (ስድብ) ያረጀ፥ የተቆራመደ።

ቆረቆንዳ ስ 1.ፍሬዎቹ ተፈልፍለው ከላዩ ላይ ከተወሰዱ በኋላ የሚቀረው የበቆሎ ፍሬዎች ተሸካሚው አካል። 2. (ዘይ.+ ስድብ) ለዛው ያለቀ፥ የተሟጠጠ (ሽማግሌ፥ አሮጊት)።

ቆረቆዘ ግ 1. ቀጨጨ፥ ጫጫ፥ ኮሰመነ። 2. ደሀየ።

ቆርቋዛ (ቆረቆዝ) ቅ ኮስማና፣ ቀጫጫ።

አቆረቆዘ ግ 1. አቀጨጨ፥ አኮሰመነ። 2. በዘበዘ፤ አደሀየ።

አቆርቋዥ ቅ በዝባዥ፣ ሌላው የደከመበትን የስራ ውጤት ያለአግባብ የሚወስድ።

ቆረበ ግ (ክር.) 1. የክርስቶስን ስጋ በላ፥ ደሙን ጠጣ፤ ስጋ ወደሙ ተቀበለ። 2. ስጋ ወደሙ በመቀበል በአንድ የትዳር ጓደኛ ተወሰነ።

ቆራቢ ቅ (ክር.) 1. ስጋ ወደሙ የሚቀበል ወይም የተቀበለ። 2. ትዳሩ ወይም ጋብቻው በቁርባን ወይም በስጋ ወደሙ የተወሰነ።

የቆራቢ እራት ስ (ክር.) የሟች ቤተሰብ በሟች ስም አዘጋጅተው ለቀዳሽ ካህናት የሚሰጡት ምግብና መጠጥ፣ ጠበል ጠዲቅ።

ቁርባን ስ (ክር.)1. ስጋ ወደሙ። 2. የሟችን ስም እየጠሩ በቤተክርስቲያን ፀሎት ለሚያደርጉ ካህናት እንዲሁም ለድሆች ይሰጥ ዘንድ በሟች ቤተሰብ የሚዘጋጅ ምግብና መጠጥ፣ ጠበል ጠዲቅ፤ መክፈልት።

ተቆረበ ግ (ክር.) 1.በቤተክርስቲያን የቅዳሴ ስንስርአት ተካሄደ፤ ተቀደሰ። 2. የቁርባን ስርአት ተካሄደ፥ ተከናወነ፤ ስጋ ወደሙ ለምእመናን ተሰጠ።

አቆረበ ግ (ክር.) 1. ስጋ ወደሙ ሰጠ፤ አቀበለ (ካህን)። 2. ወደ ቤተክርስቲያን ወስዶ ስጋ ወደሙ እንዲቀበል አደረገ (ቤተሰብ ልጅን ወይም አቅመደካማ የሆነን ሰው)።

አቁራቢ ቅ (ክር.) ለቆራቢዎች ስጋ ወደሙ ያቀበለ ወይም የሚያቀብል ካህን።

ያቁራቢ ስ (ክር.) ለአቁራቢዎች (ለቀደሱና ስጋ ወደሙ ላቀበሉ ካህናት) የሚሰጥ ምግብና መጠጥ ወይም ገንዘብ።

አስቆረበ ግ (ክር.) 1. በቤተክርስቲያን ተገኝቶ የቅዳሴው ስነስርአት እስኪያልቅ ድረስ የፀሎቱ ተካፋይ ሆነ። 2. ፀበል ፃዲቅ በሟች ስም እያዘጋጀ ለካህናትና ለነዳያን በመስጠት የሟችን ስም በፀሎት አስጠራ፣ በሟች ስም ቅዳሴ አስቀደሰ።

አስቆራቢ ቅ (ክር.) በሟች ስም ቅዳሴ እንዲቀደስ፥ ቁርባን እንዲቆረብ በማድረግ የሟችን ስም በፀሎት የሚያስጠራ (የሟች ቤተሰብ)።

*ቆረበበ

ቆርባብጭ (ቁርባብጭ፥ ቁርብጭ) ስ ከቆዳ ወይም ከጨርቅ የተሰራ ክረቢት።

ቆርባባ (ቆረበብ) ቅ ጎርባባ፥ ኮርፋፋ።

ተንቆረበበ ግ ተንኮረፈፈ፥ ተንጎረበበ።

አንቆረበበ ግ አንኮረፈፈ፥ አንጎረበበ።

ቆረበጨ ግ አተረ፡ አበጠ፡ ጎረበ፡ ውሃ ያዘ፡ ወይም አዘለ (የሰውነት ቆዳ)።

ቁርብጭታ ስ እትራት፡ እበጥ።

አቆረበጨ ግ ቆረበጨ።

ቆረባ ግ ደረቀ፥ ገረረ።

ቆርባ ቆርባ አለ ግ ተንቆራባ።

ተንቆራባ ግ እንደ ደረቀ ቆዳ ተንኳኳ፥ ተንጓጓ።

አንቆራባ ዝ.ክ.

ቆርባብጆ "ቆረበበ" ስር ተመ.

ቆረነ ግ 1. ወሰን፡ ድንበር ለመከለል ድንጋይ ተከለ፡ ምልክት አበጀ። 2. ሰብሉን አጭዶ በማንሳት ማሳው ቆረን እንዲሆን አደረገ።

ቆረን (ቁረን) ስ 1. ጤፍ፡ ስንዴ፡ ገብስ፥... ከታጨደ በኋላ ማሳው ላይ የሚቀረው የሰብሉ አገዳ። 2. ሰብሉ ታጭዶ ባዶውን የቀረ ማሳ።

ቆረንጮ "ቁረንጮ" ን ተመ.

***ቆረኘ**

ቁራኛ ስ 1- ከዳኛ ዘንድ እስኪደርስ ወይም እስኪፈረድ ድረስ፡ እግሩ ወይም እጁ ከጠላቱ እግር ወይም እጅ ጋር እንዲጣመር ተደርጎ ከጠላቱ ጋር በአንድነት ይታሰር የነበረ ሰው። 2.(ዘይ.) የማይለቅ፡ አብሮ የሚኖር እንደ ዛር፥ ርኩስ መንፈስ ያለ በሽታ።

ተቆራኘ ግ 1. እጁ ወይም እግሩ ከጠላቱ እግር ወይም እጅ ጋር እንዲጣመር ተደርጎ ታሰረ። 2. (ዘይ.) አልተውም፥ አልለይም፥ አልነጠልም ብሎ አብሮ ሆነ።

አቆራኘ ግ 1. አንዱን ከሌላው ጋር አጣምሮ አሰረ። 2. ከ___ጋር አብሮ እንዲኖር፥ ከእርሱ እንዳይለይ፡ እንዳይነጠል አደረገ።

***ቆረዘዘ**

ቁርዝዝ አለ ግ ተንቆረዘዘ።

ተንቆረዘዘ ግ ሊወርድ፡ ሊፈስ ተቃረበ፥ ተንጠለጠለ (እንባ፥ ጤዛ፡...)።

አንቆረዘዘ ግ ሊያወርድ፥ ሊያፈስ፥ ሊያዘንብ ተቃረበ፥ አዘለ (ደመና ዝናብን፥ አይን እንባን፥...)።

ቆረጠ ግ 1. በጣ፥ ሰነበጠ፡ ሰነጠቀ፥ ቀደደ (ስለት አካልን)። 2. ጎመደ፡ ጎረደ፡ በጠሰ። 3. መደመደ፥ አሳጠረ፤ ከረከመ፥ አስተካከለ (ፀጉርን፡ አታክልትን፥...)። 4. ወሰነ፥ ጨከነ (አንድ ነገር ለማድረግ ወይም ላለማድረግ)። 5. ከተሰጠው ጥቅል ገንዘብ ላይ ለእቃው ወይም ለአገልግሎቱ መከፈል ያለበትን ያህል ሂሳብ ቀንሶ ወሰደ (ገንዘብ ተቀባይ)። 6. ገዛ ወይም ሸጠ (ትኬትን)። 7. ወሰነ፡ በየነ፥ አሳጠረ (ነገርን)። 8. የቀጠሮ ቀን ወሰነ፥ አበጀ። *ቀን ቆረጠ*። 9. ቀጠፈ (ቅጠልን፥ ፍሬን ከዛፍ ላይ)። 10.ማርን ከቀፎ ሰበሰበ፡ አወጣ። *ማር የሚቆረጠው በምን ወር ነው?* 11. ጨረሰ፡ ፈፀመ (በመስራት ላይ የነበረን ሸማ፥ ስፌት)።12. አመመ፡ አሰቃየ። *ሆዴን ቆረጠኝ*። 13. (ዘይ.) ቆጨ፥ ከነከነ። *ያን ሆድህን ከሚቆርጥህ ሁሉን ተናገረውና ይወጣልህ*።

ቆርጦ ቀጥል ቅ ውሸታም፡ ወሬው የማይታመን (ሰው)።

መቁረጪት ስ አነስተኛ መቀስ።

መቁረጫ ስ 1. ለመቁረጥ የሚያገለግል ስለት ያለው መሳሪያ። 2. የመጨረሻ ልጅ። *መቁረጫዬ ሴት ልጅ ናት*።

ቁራጭ ቅ የአንድ ነገር ክፋይ፥ ጉማጅ፥ ብጣሽ።

ቁራጭያም ቅ (ስድብ) ምናምንቴ፥ የሰው ጎደሎ፡ ብጣሻም።

ቁርጣ ስ በመጀመሪያው እርሻ ጊዜ መሬቱ የታረሰው ከታች ወደ ላይ ከላይ ወደታች እየተባለ ከሆነ፥ በድጋሚው ጊዜ የዚህ ተቃራኒ የሆነ አቅጣጫ ተከትሎ የሚደረግ የአስተራረስ አይነት።

ቁርጥ ቅ 1. እርግጠኛ፡ ትክክለኛ። *ቁርጡ አልታወቀም*። 2. የማይቀር፡ መደረግ ያለበት፥ የመጨረሻ ውሳኔ። *ዘንድሮ ቁርጥ ነው፤ ትዳር እመሰርታለሁ*። ስ 3. ሳይቀቀል ወይም ሳይጠበስ ጥሬውን የሚበላ የከብት ስጋ፡ እርጥብ ወይም ቁርጥ ስጋም ይባላል።

ቁርጥ ስራ ስ በተወሰነ ገንዘብ የሚሰራ የተወሰነ የስራ መጠን።

ቁርጠት ስ የሆድ ውስጥ የህመም ስሜት አይነት።

ቁርጠኛ ቅ 1. እርግጠኛ። 2. ወደሗላ የማይል፡ የማያወላውል (አንድ ነገር ለማድረግ)።

ቁርጠኛ ዘመድ ስ ታማኝ፥ የማይከዳ፥ ለክፉ ጊዜ የሚደርስ ዘመድ፡ ወዳጅ።

ቆራጣ ቅ (ስድብ) 1. አካለ ጎደሎ፡ አካሉ ሙሉ ያልሆነ። 2. እንከን ያለበት፥ ያልተሟላ፥ ጎደሎ (ነገር)።

ቆራጥ ቅ ደፋር፥ ጎበዝ፡ የማያወላውል፥ በውሳኔው የሚፀና።

ቁርጥራጭ ቅ ብጥስጣሽ፥ ክፍልፋይ፥ ከተቆራረጠ ነገር ላይ የተራረፈ።

ቁርጥርጥ አለ ግ ተቆራረጠ።

ቁርጥርጥ አደረገ ግ አንድን ነገር ብዙ ቦታ ላይ ቆረጠ፥ ጎመደ።

ተቆረጠ ግ ተጎረደ፥ ተጎመደ፥ ተበጠሰ።

ተቆራጭ ቅ 1. በተወሰነ ጊዜ የሚከፈል ወይም የሚሰጥ መተዳደሪያ ገንዘብ (ለምሳሌ ለወላጅ ወይም ለልጅ ማሳደጊያ)። 2. ከሙሉ ሂሳብ ወይም ገንዘብ ላይ ተከፋይ ሆኖ የቀረ ወይም የሚቀር (ገንዘብ)።

ተቆራረጠ ግ 1. ብዙ ቦታ ላይ ተቆረጠ፡ ተበጣሰ፥ ተጎመደ። 2. በጠብ፡ በቂም ወይም በሌላ ምክንያት ተለያየ፡ ተራራቀ፡ ግንኙነት አቆመ።

ተቋረጠ ግ 1. ቆመ፡ ቀረ። *መብራት ተቋረጠ።* 2. የተወሰነ ስራ ለመስራት ተዋዋለ፡ ተከናተረ።

ተቋራጭ ስ ውሉታ በመዋዋል የተወሰነ ስራ እየተረከበ የሚሰራ፥ ተከናታሪ።

አቆረጠ ግ አቆመ፡ ተወ (ለምሳሌ. ዝናም፡ የወር አበባ)።

አቆራረጠ ግ 1. አቀያየመ፡ አጣላ። 2. በአቋርጥ፥ በአቋራጭ መንገድ ሄደ።

አቆራራጭ ቅ 1. አጭር (መንገድ)። 2. የሚያጣላ።

አቋረጠ ግ 1. አቆመ፡ ተወ። *ትምህርቱን አቋርጦ ስራ ያዘ።* 2. በአጭር መንገድ ሄደ፤ አሳበረ። 3. ተሻገረ፡ ሰንጥቆ አለፈ። *ወንዙን አቋርጦ ሄደ።* 4. አደናቀፈ፡ በንግግር መሃል ጣልቃ ገባ።

ማቋረጫ ቅ 1. አጭር የሆነ (መንገድ)። 2. ማስቆሚያ፡ መጨረሻ። *ወሬው ማቋረጫ የለውም።*

አቋራጭ [መንገድ] ስ ወደሚሄዱበት ቦታ በቶሎ የሚያደርስ አጭር መንገድ።

በአቋራጭ በአጭሩ፡ ባልተለመደ፥ ባልተገመተ ዘዴ፥ አኳኋን፡ መንገድ። *በአቋራጭ ስልጣን ላገኘ።*

አስቆረጠ ግ 1. አስጨረሰ፡ የመጨረሻውን ቃል ወይም ሃሳብ አገኘ፥ አስወሰነ። 2. ገዛ (ትኬትን)።

ቆረጠመ ግ 1. በጥርስ ሰባበረ፥ አደቀቀ፥ በላ (ጥራጥሬን፡ አጥንትን)። 2. አመመ (ሰውነትን)።

ቁርጥማት ስ የአጥርን፥ የእጅን፥... ውስጠኛ ክፍል የሚነትግት የህመም አይነት።

***ቆረጠጠ**

ቆርጣጣ (ቆረጠጥ) ቅ ከጭንቀት፡ ከንዴት፡...የተነሳ ቁጭ ብድግ፡ ሄድ መጣ፡ ገባ ወጣ የሚል፡ የሚቁነጠነጥ(ሰው)።

ቆርጠጥ ቆርጠጥ አለ ግ ከጭንቀት፥ ከንዴት፡... የተነሳ ቁጭ ብድግ፥ ሄድ መለስ፡ ወጣ ገባ አለ፡ ተቁነጠነጠ፡ ተንቆራጠጠ።

ተንቆራጠጠ ግ ከጭንቀት፡ ከንዴት፡... የተነሳ ቁጭ ብድግ፡ ሄድ መለስ፡ ወጣ ገባ አለ፥ ተቁነጠነጠ።

አንቆራጠጠ ግ 1. አንጎራደደ፡ ወዲያና ወዲህ አለኝ፡ አሳሳርፍ አለ። 2. ወዲያና ወዲህ ወሰደ፥ ከቦታ ወደቦታ አዘዋወረ፡ አንድ ቦታ ላይ እንዳይቆይ አደረገ። 3. (ዘይ.) አስጨነቀ፡ አሰቃየ።

ቆረጨመ (ቀረጨመ) ግ ቆረጠመ፡ አደቀቀ፥ ሰበረ (በጥርስ)።

ቆረፈደ ግ ደረቀ፥ ሻካራ ሆነ፥ ልስላሴ አጣ።

ቆርፋዳ (ቆረፈድ) ቅ 1. የደረቀ፥ ሻካራ። 2. (ዘይ.) አመለ መጥፎ፥ ባታራ።

ቁርፍድ ቅ ቆርፋዳ።

ተቆራፈደ ግ 1. ደረቀ፡ ሻከረ፡ ልስላሴ አጣ። 2. ጠባዩ መጥፎ ሆነ። 3. በችግር ተቆራመደ።

አቆራፈደ ግ በችግር አቆራመደ፥ አማቀቀ።

***ቆረፈፈ**

ቆረፈፍ (ቆርፋፋ) ቅ ኮርፋፋ።

ተንቆረፈፈ ግ ተንኮረፈፈ።

አንቆረፈፈ ግ አንኮረፈፈ።

ቆሬ (ቆሬ) ስ በጣም ወይም በደቃ አምሳያ እንደ ዋንዛ ካለ ግንድ እየተጠረበ የሚሰራና ለውሃ መያዣ፡ ለማስታጠቢያ፥... የሚያገለግል የቤት እቃ፤ ገበቴ።

ቆሬ

ቆራ^{1} ግ 1. በስለት ሰውነት ላይ በጣ፥ ምልክት አደረገ። 2. በብትር መታ፤ ቆረመ። 3. በትንሹ ላጨ፤ በቀረ።

ቆራ^{2} "**ቆረረ**^{2}" ስር "**ቁር**" ን ተመ.

ቆራቢ "**ቆረበ**" ስር ተመ.

ቆራጣ "**ቆረጠ**" ስር ተመ.

ቆራጥ ዝ.ከ.

ቆሬ "**ቆሬ**" ን ተመ.

ቆርማዳ "***ቆረመደ**" ስር ተመ.

ቆርሳሳ "***ቆረሰሰ**" ስር ተመ.

ቆርቆሮ ስ 1. በቀላሉ ሊተጣጠፍ የሚችልና የሚብለጨለጭ እንደ ብረት ያለ የማእድን አይነት። 2. ከላይ ከተጠቀሰው የማእድን አይነት የሚሰራ ስስ የሆነ የጣሪያ መክደኛ። 3. ከላይ ከተጠቀሰው የማእድን አይነት በተለያየ ቅርፅ የሚሰራ፥ በውስጡ ፈሳሽ ወይም ጠጣር ነገሮችን

ለመያዝ የሚያገለግል እቃ።

ቆርቆሮ ራስ ቅ (ዘይ.፣ ስድብ) ደደብ፣ ማስተዋል፣ ማመዛዘን የሚሳነው።

ቆርቆሮ ቤት ስ ጣሪያው በቆርቆሮ የተሸፈነ ወይም ጣሪያውም ግድግዳውም በቆርቆሮ የተሰራ ቤት።

የቆርቆሮ ምግብ ስ በፋብሪካ ውስጥ የሚዘጋጅና በቆርቆሮ ውስጥ እየታሸገ ለተጠቃሚው የሚቀርብ ምግብ።

ቆርባባ "*ቆረበበ" ስር ተመ.

ቆርኪ (ቆርኪ) ስ ከቆርቆሮ የተሰራ የጠርሙስ አፍ ማሸጊያ፣ መክደኛ።

ቆርኬ ስ ከትከሻው ከፍ ከዳሌው ኣጠር የሚል፣ ቀላ ያለ ቡናማ መልክ ያለው፣ ጫፋቸው ወደ ውስጥ ጎበጥ የሚሉ ቀንዶች ያሉት፣ ጠበብ ያለ ረዥም ፊትና ከቀንዶቹ መነሻ ላይ ጉብር ያለ አጥንት ያለው፣ ሳር በል የሆነና በቆላ አካባቢ በመንጋ የሚኖር የዱር እንስሳ(ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።

ቆርጣጣ "*ቆረጠጠ" ስር ተመ.

ቆርፋዳ "*ቆረፈደ" ስር ተመ.

ቆርፋፋ "*ቆረፈፈ" ስር ተመ.

ቆሮ "አባ ቆሮ" ን ተመ.

ቆሰለ ግ 1. በጦርነት፣ በጠብ ወይም በሌላ ምክንያት አካሉ ላይ ጉዳት ደረሰበት፣ ተሳጠ፣ ተወጋ፣ ደማ፣...። 2. ቁስል ያዘ፣ አበጀ (አካል)። 3. (ዘይ.) በሃዘን፣ በንዴት፣ በመጥፎ ነገር፣... ምክንያት ስሜቱ ተጎዳ፣ ተነካ፣ በጣም ተናደደ።

ቁስል ስ 1.በመቆረጥ፣ በመወጋት፣... ምክንያት ተጎድቶ የሚደማ ወይም የሚመግል የሰውነት ክፍል። 2. (ዘይ.) ቁርሾ፣ ቂም፣ መጥፎ ትዝታ፣ እንከን። *በመካከላቸው የኖረ ቁስል ሻረ።*

ቁስሉ ደረቀ 1. ሻረ፣ ዳነ።2. ቁርሾው ተተወ፣ እርቅ ወረደ።

ቁስለ ስጋ ስ የአካል መቁሰል፣ ቁምጥና፣ ደዌ ስጋ።

ቁስለት ስ ንዝንዝ፣ ጭቅጭቅ፣ ንዴት ፣ ብስጭት።

ቁስለኛ ስ በጦርነት ወይም በሌላ አደጋ ምክንያት አካሉ ላይ ጉዳት የደረሰበት ሰው።

ተቆሳሰለ ግ (ዘይ.) ተጣላ፣ ቂም ተያያዘ።

ተቋሰለ ዝ.ክ.

አቁስል ቅ አናዳጅ፣ አብግን። *ልጁ ኣቁስል ነው።*

ቆሰቆሰ ግ 1. ማገዶን ወደ እሳት ውስጥ ገፋ፣ ጨመረ። 2. (ዘይ.) ጫረ፣ ጀመረ (ነገርን፣ ጠብን)።

መቆስቆሻ ስ ማገዶን (ደቃቅ እንጨትን፣ ፍግን) ወደ እሳት ውስጥ መግፊያ፣ መጭቆሻ (ቀጫጫ እንጨት ወይም ብረት)።

ቆስቋሽ ቅ 1. ማገዶን (እንጨትን፣ ኩበትን፣...) ወደ እሳት ውስጥ የሚገፋ፣ የሚጨምር። 2. (ዘይ.) ጠብ ጫሪ።

ተቆሳቆሰ ግ ተሟሟታ፣ ተዋጋ፣ ተንደደደ፣ ተፋጀ፣ ተባለቀ።

አቆሳቆሰ ግ አሟሟታ፣ አዋጋ፣ አፋጀ፣ አስተባለቀ።

ቆሸመደ ግ ከሳ፣ አቅሙ ቢስ ሆነ።

ቆሸማዳ (ቆሸመድ) ቅ (ስድብ) አቅመቢስ፣ ደቃቃ፣ ከሲታ።

ቆሸሸ ግ አደፈ፣ ፅዳት አጣ፣ ንፅህና ጎደለው።

ቆሻሻ (ቁሻሻ) ቅ 1.ንፅህና፣ ፅዳት የሌለው። ስ 2. ጥራጊ፣ እድፍ፣ ጉድፍ። 3. (ዘይ.፣ ስድብ) ሀ- ንፅህናውን ወይም ፅዳቱን የማይጠብቅ። ለ- በግብሩ፣ በጠባዩ ብልሹ የሆነ፣ ልክስክስ።

የቆሻሻ መኪና ስ ተጠራቅሞ የሚቆየውን ቆሻሻ ስብስቦ እየወሰደ ከመኖሪያ አካባቢ ራቅ ብሎ በሚገኝ በተወሰነ ቦታ ላይ የሚጥል መኪና።

የቆሻሻ መጣያ ስ 1. የሚያስቀይሙ፣ ለጤና ጠንቅ የሆኑና በቆሻሻ ደረጃ የሚታዩ ነገሮች እየተወሰዱ የሚጣሉበት ከመኖሪያ አካባቢ ራቅ ብሎ የሚገኝ የተወሰነ ቦታ። 2. እንደ ቅርጫት፣ በርሚል፣... ያለ ጊዜያዊ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ።

ተንቋሸሸ ግ ተጥላላ፣ በመጥፎነት ወይም በቆሻሻነት ታየ።

አንቋሸሸ ግ የአንድን ነገር መጥፎነት ወይም ቆሻሻነት በመናገር አጥላላ፣ አናናቀ፣ አኪያኪያሰ።

ቆሸቆሸ ግ 1. ከመጠን በላይ ደረቀ፣ ገረረ። 2. (ዘይ.) በጣም አረጀ፣ ሰውነቱ ደረቀ።

ቆሽቋሻ (ቆሸቆሽ) ቅ 1. ከመጠን በላይ ከመድረቁ የተነሳ በቀላሉ ሊሰበር የሚችል። 2. (ዘይ.፣ ስድብ) በጣም ከማርጀቱ ወይም ከመጎዳቱ የተነሳ ሰውነቱ የደረቀ፣ አቅም የሌለው፣ ቀሸማዳ።

ተንቆሻቆሸ ግ 1. ከመጠን በላይ ደረቀ፣ ገረረ። 2. በጣም ከማርጀቱ የተነሳ ሰውነቱ ደረቀ፣ አቅመ ቢስ፣ ቀሸማዳ ሆነ፣ ጠነጠነ።

አንቆሻቆሸ ግ 1. ከመጠን በላይ እንዲደርቅ፣

እንዲገር አደረገ። 2. አደቀቀ፥ ሰባበረ፡ አንቋቋ (የተጎዳ ሰውነትን በማሸት ወይም በመጫን)።

እንቁሽቁሽ ቅ ደረቁቻ፡ ደቃቃ፡ አቅመ ቢስ።

ቆሸበ ግ የምግብ ፍላጎት አጣ፡ ከሳከሰ።

ቆሻባ (ቁሽብ) ቅ ምግብ የማይደፍር፡ በሚገባ የማይበላ።,

ቁሽቢያም ዝ.ከ.

***ቆሸበለ**

ተንቆሻበለ ግ ተቀማጠለ።

አንቆሻበለ ግ አሽበለበለ፡ አቀማጠለ።

ቆሸንዳ ስ ከሲታ፡ ደረቁቻ።

ቆሸደ ግ ደረቀ (እንጀራ)።

ቆሽድ ስ የደረቀ እንጀራ፡ ኮቸሮ።

ቆሻሻ "ቆሸሸ" ስር ተመ.

ቆሻባ "ቆሸበ" ስር ተመ.

ቆሸማዳ "ቆሸመደ" ስር ተመ.

ቆሸቋሻ "ቆሸቆሸ" ስር ተመ.

ቆሽት ስ በአፈጣጠሩ ከጨጓራ ጋር የተያያዘ ሆኖ የደቀቀና የላመ ምግብ የሚገኝበት ከረጢት መሰል የሰውነት ክፍል።

ቆሽቱ አረረ በጣም ተናደደ፡ ተበሳጨ።

ቆሽት አንድድ አናዳጅ፥ አብሻቂ።

ቆቀር ስ ትንሽ ፍሬ ወይም እንኳር(የእጣን፥ የአፈር፡...)።

ቆቅ ስ 1. መጠኗ ዶሮ የሚያህል፡ በጫካ የምትኖር፡ ሰዎች በወጥመድ እየያዙ እንደ ዶሮ የሚበሏት የአእዋፍ ዝርያ(በአሉን ወፍ ስር ተመ.)። 2. (ዘይ.) ንቁ፡ ጠርጣራ፡ ጠንቃቃ፡ ብልጥ።

ቆቅማ ቅ ህብረ ቀለሙ ቆቅ የሚመስል።

ቆበር ስ በበሽታ ወይም በሌላ ምክንያት በአፍ ዙሪያ የሚታይ አረፋ መሰል ምራቅ።

ቆበሩን ደፈቀ 1. ከአፉ ብዙ ምራቅ ጠጣ ወይም አወጣ (ብዙውን ጊዜ በህመም ምክንያት)። 2. (ዘይ.) የማይጠቅም ተገቢ ያልሆነ ነገር ተናገረ፡ ለፈለፈ።

ቆበራም ቅ (ስድብ) ቆበር ያለበት፡ ቆበር የሚደፍቅ።

***ቆበቆበ**

አቆበቆበ ግ 1. አጎረበ፡ አጎበጎበ፡ አቆረበጠ። 2.አኮበኮበ፡ ዝግጁ ሆነ (ለመሄድ፡ ለመናገር፡...)።

አቆብቋቢ ቅ ለመሄድ፡ ለመናገር፡... የተነሳ፡ ተዘጋጅቶ በመጠበቅ ላይ ያለ።

ቆባ¹ ስ የአተር፡ የባቄላ፡...ፍሬ ሽፋኑን፥ እንቁርባ።

ቆባ² ቅ 1. ለፍላፊ፥ ምላሰኛ። 2. ንቁ፥ ባለሙያ (ሴት)።

ቆብ ስ 1. ከጨርቅ ወይም ከክር የሚሰራና መነኩሴ ወይም መንፈሳዊ ሰው ራሱ ላይ የሚደፋው አስኬማ። 2. ለፀሃይ ወይም ለብርድ መከላከያ ራስ ላይ የሚደረግ ኮፍያ።

ቆብ 1ኛ ቁ.

ቆቡን ቀደደ/ጣለ ምንኩስናውን ትቶ አለማዊ ሆነ፡ ስልጣኑን አፈረሰ።

ቆብ ደፋ 1. ቆብ ራሱ ላይ አደረገ፡ ራሱን ወይም ጭንቅላቱን በቆብ ሸፈነ። 2. መነኮሰ፡ ቆብ ጫነ።

ቆብ ጫነ መነኮሰ።

የቆብ ተዝካር ስ የመነኮሱ ሰዎች በመነኮሱበት እለት ወይም በመነኮሱ በአርባኛው ቀን ወይም በየአመቱ፥ በሞተ ሰው አምሳያ በስሙ ፍትሃት ከተደረገላቸው በኋላ ለካህናትና ለነዳያን የሚያበሉት ድግስ፥ ተዝካር።

የቆብ አባት ስ አንድ ሰው በሚመነኩስበት ጊዜ፡ በተዘጋጀለት ቆብ ላይ ፀሎት አድርጎ ቆቡን ራሱ ላይ የሚደፋለት ድንግላዊ መነኩሴ፥ አመንኳሽ።

ቆቦ ስ በፍሬው መሸፈኛ ውስጥ ነጭ ሃር የሚመስል ብዙ ያለው፡ በቆላ የሚገኝና ወተታም የሆነ የእፅዋት አይነት።

***ቆተቸ**

ቁትቻ ስ ውርርድ።

ተቆታች ግ ተወራረደ።

አቆታች ግ አወራረደ።

ቆቻ ስ ብርታት፡ ጥንካሬ።

ቆቻ ዋለ ከቀትር በፊት ከአንድ በሬ ጋር፥ ከቀትር በኋላ ደግሞ ከሌላው በሬ ጋር በመጠመድ ምንም ድካም ሳያሳይ ቀኑን ሙሉ በጥንካሬ አረሰ (ጎበዝ የሆነ በሬ)።

ቆነሰ ግ በጣም ገማ፡ ሸተተ፡ ከረፋ፡ ጠነባ።

ቁናስ ስ ግማት፥ ክርፋት።

ቁናሳም ቅ (ስድብ) ግማታም፥ ክርፋታም።

ቆነቆነ ግ ነቀዘ፥ ጠነበነ።

ቁንቁን (ቁንቁኔ) ስ ነቀዝ፡ ጥንጣን፡ አንዳንድ የደረቁ የእንጨት አይነቶችን ውስጣዊ አካል እየበረበረ በመብላት ለብልሽት የሚዳርግ

የትል ወይም የነፍሳት አይነት።

ቆነቆነ^2 ግ ሰሰተ፥ ቀቀተ።

ቁንቋና ቅ ስስታም፥ ንፉግ፥ ቅቅታም።

ተቆናቆነ ግ ሰሰተ፤ ተንቆጣቆጠ።

ቆነቆነ^3 ግ በጥቃቅኑ ከተፈ፤ መተረ።

መቆናቆን ስ ዱለት።

ቆነነ^1 ግ ጎነጎነ፥ ሸረበ፥ ታታ (ፀጉርን፣ ጭራን፣...)።

ቆናኝ ስ ፀጉር ሰሪ፣ ሹሩባ ሰሪ።

ቆነነ^2 ግ ጀነነ፣ ኮፈሰ፣ አኮራ። *ምን ይቆንንሃል ራመድ ራመድ በል እንጂ።*

ቁንን ቅ ጅንን፣ ኩሩ።

ተቆነነ ግ ተጀነነ፤ ተኮፈሰ፤ ኮራ።

ቆነነ^3 ግ እየለካ፣ እየመጠነ፣ እየሰፈረ ሰጠ (የቀለብ እህልን፥ ድርጎን)።

መቁነን ስ በገዳም ውስጥ በማህበር ለሚኖሩ መነኮሳት በቀን አንድ ጊዜ ተለክቶና ተመጥኖ ወይም ተሰፍሮ የሚሰጥ ምግብ፣ ድርጎ።

ቆናኝ ቅ መቁነን እየለካ ለድርጎኛ የሚሰጥ፥ አዳይ፥ አከፋፋይ።

ተቆነነ ግ መቁነን ታደለ፤ ተሰጠ፤ መቁነን አገኘ፥ ተቀበለ።

ቆነደለ ግ ሹሩባ ሰራ፥ ጎነጎነ፥ ቆነነ (ፀጉርን)።

ቆንዳላ (ቁንዳላ) ስ ሹሩባ የተሰራ ፀጉር።

ቆነደደ^1 ግ ሹሩባ ሰራ (ጎፈሬ ሆኖ የቆየውንና እስከዚህም ርዝማኔ የሌለውን ፀጉር እየሳበ)።

ቁንድድ(ቁንድዶ) ስ 1. የአጭር ፀጉር ሹሩባ። ቅ 2. ጎፈሬ ሆኖ የቆየውን ፀጉር ሹሩባ ያደረገች፥ የተሰራች። 3. ፀጉረ አጭር።

ቆንዳዳ ቅ አጭር፣ ሽክራና ቁጥርጥር ፀጉር።

ቆነደደ^2 ግ 1.በጆሮ፥ በአሰንጋ ገረፈ፣ በለበት መታ። 2. አሰቃየ (ብርድ፣ ረሃብ፣...)። 3. (ዘይ.) ቀጣ። *ጥፋተኛውን መቶ ብር ቆነደደው።*

ቆነጀ ግ አማረ፣ ተዋበ፤ መልከመልካም ሆነ።

ቆነጀች ለአቅመ ሄዋን ደረሰች።

ቁንጅና ስ ውበት፣ ደምግባት፥ መልከ መልካምነት።

የቁንጅና ሳሎን ስ የሴቶችን ፀጉር የሚተኩስ፥ የሚሰራና የውበት አገልግሎት የሚሰጥ ንግድ ቤት።

ቆንጆ ቅ 1.ውብ፣ ጥሩ፤ ሸጋ፥ ያማረ። ስ 2.ለአቅመ ሄዋን የደረሰች ልጃገረድ።

ተቆነጃጀ ግ ተዋበ፣ አማረ፣ ራሱን አስዋበ፣ አሳመረ።

አቆነጀ ግ አስዋበ፤ አሳመረ።

ቆነጎለ "ጎነቆለ"ን ተመ.

ቆነጠረ ግ 1. በጥቂቱ አነሳ (ለመውሰድ ወይም ለመስጠት)። 2. ወጋ፥ ቆነጠጠ፣ በጨቀ።

ቁንጣሪ ስ ብዙት ካለው ነገር ላይ በጥቂቱ ወይም በትንሹ ተከፍሎ የተነሳ፣ ጥቂት፣ ትንሽ ነገር።

***ቆነጠረ**

ቆንጣራ ቅ በትንሽ ነገር በመቆጣት ተነስቶ በፍጥነት የሚሄድ፣ ቁጡ።

ቁንጥር ቁንጥር አለ ግ ቆጣ ቆጣ አለ፤ በንዴት፤ በቁጣ መንፈስ ተራመደ።

ተቆናጠረ ግ በቁጣ መንፈስ፣ በንዴት ተናገረ ወይም ተራመደ።

አቆናጠረ ግ ቆጣ ቆጣ አሰኘ፣ አስደረገ ወይም በቁጣ መንፈስ አራመደ።

***ቆነጠነጠ**

ቁንጥንጥ (ቆንጥናጣ) ቅ ቅብጥብጥ፣ ሰውነቱ አንድ ቦታ ላይ ረግቶ የማይቀመጥ።

ቁንጥንጥ አለ ግ ተቁነጠነጠ፣ ተቅበጠበጠ።

ቁንጥንጥ አደረገ ግ አቁነጠነጠ፥ አቅበጠበጠ።

ተቁነጠነጠ ግ ተቅበጠበጠ፣ እረፍት፣ እርጋታ አጣ።

አቁነጠነጠ ግ አቅበጠበጠ፥ እረፍት፥ እርጋታ አሳጣ።

ቆነጠጠ ግ 1. በእጅ ጣቶች ወይም በሌላ ነገር ሰውነትን አጥብቆ በመያዝ አሳመመ። 2. በእግር ጣቶች አጥብቆ ያዘ (እርካብን፣ መሬትን)። 3. በጉጠት፣ በመቆንጠጫ አጣብቆ ያዘ። 4.(ዘይ.) ቀጣ፣ ስርአት ይዞ እንዲያድግ አደረገ(ልጅን)። 5. ቆጥቦ፣ ሰስቶ ያዘ፣ አጠራቀመ (ሃብትን፣ ገንዘብን፣...)። 6.(ዘይ.) የሴቷን ገላ በጣት በመቆንጠጥ ለፍቅር ጉዳይ እንደሚፈልጋት ምልክት ሰጣት።

ቆንጥጣለች አርግዛለች።

ቆንጥጦ አጠበ ልብሱን፣ ጨርቅን ሙሉ በሙሉ ሳይሆን ቆሻሻ የነካውን ክፍል ብቻ አጠበ።

መቆንጠጫ ስ 1. ፍምን ወይም የጋለ ብረትን ቆንጥጦ ለመያዝና ከአንድ ቦታ ወደሌላው ለማዘዋወር እንዲረዳ የሚዘጋጅ፣ መንታ ጫፍ ያለው የንዳ ወይም ብረት። 2. ገመድ ላይ የተሰጣ ልብስ እንዳይወድቅ፥ ከገመዱ ጋር አጣብቆ እንዲይዝ ሆኖ የተሰራ መንታ ጫፍ ያለው እንጨት ወይም ሌላ ቁሳቁስ።

ቁንጥጫ (ቁንጢጥ) ስ 1. በአመልካች ጣትና በአውራ ጣት አማካይነት ሰውነትን በሃይል አጥብቆ የመያዝና የማሳመም ድርጊት። 2. የእጆችን የመዳፍ ጀርባዎች በጣት ቆንጥጦ

በመያዝና አንዱን በአንዱ ላይ በማነባበር፡ እንዲሁም የተነባበሩትን በማለያየትና እንደገና ድርጊቱን በመድገም የሚካሄድ የልጆች ጨዋታ።

ቆንጠጥ አለ ግ ጠንቀቅ፡ ኮስተር አለ።

ተቆነጠጠ ግ ተቆጣ፥ ስነስርአት እንዲኖረው ተደረገ።

ተቆንጥጦ ያደገ አስተዳደጉ መልካም የሆነ፡ ጨዋ፡ ስነስርአት ያለው።

ያልተቆነጠጠ ባለጌ፡ ስነ ስርአት የሌለው (ልጅ)።

ተቆናጠጠ ግ 1. በጣቶቹ ሰውነትን አጥብቆ በመያዝ አሳመመ። 2. ተደላደለ፡ መሰረት ያዘ፡ ተቋቋመ (ለኑሮ)።

መቆናጠጫ ስ መቋቋሚያ፥ መነሻ (ገንዘብ)።

አቆናጠጠ ግ አቋቋመ፡ አደላደለ፡ አጠናከረ (አስፈላጊውን እርዳታ በማድረግ)።

ቆነጥናጣ "***ቆነጠነጠ**" ስር "**ቁንጥንጥ**"ን ተመ.

ቆነጨ ግ ቁንጫ አፈራ፡ ፈጠረ፡ ቁንጫ ሆነ (ቤቱ)።

ቁንጫ ስ ተፈናጣሪና ዘላይ የሆነች፡ ቅማል የምታህል፥ ብዙውን ጊዜ ጽዳቱ በሚገባ ባልተጠበቀ መኖሪያ ቤት ውስጥ የምትገኝ ጥቁር ቡናማ ተባይ።

ቁንጫ

ቆነፀለ ግ ስለ አንድ የእውቀት ዘርፍ በጥቂቱ ወይም በቁንፅሉ አወቀ፥ ተማረ፥ ተረዳ።

ቁንፅል ቅ ሙሉነት የሌለው፡ ጎደሎ።

ቁንፅልፅል ቅ ያልተሟላ፡ ብዙ ነገር የጎደለው።

ቆናኝ^1 "**ቆነነ**^{1}" ስር ተመ.

ቆናኝ^2 "**ቆነነ**^{3}" ስር ተመ.

ቆንሲል ስ የአገሩን መንግስት በመወከል በሌላ አገር የሚቀመጥ ተወካይ፡ ጉዳይ ፈፃሚ።

ቆንቋና "**ቆነቆነ**^{2}" ስር ተመ.

ቆንዳላ "**ቆነደለ**" ስር ተመ.

ቆንዳዳ "**ቆነደደ**" ስር ተመ.

ቆንጆ "**ቆነጀ**" ስር ተመ.

ቆንጣራ "***ቆነጠረ**" ስር ተመ.

ቆንጥር ስ የሚነክሰውን ሌላ አካል ወይም ገላ የሚቦጭቅ ቆሳፋ እሾህ ያለው የእፅዋት አይነት።

ቆዘመ ግ 1. አዘነ፡ ተከዘ። 2. አለቀሰ፡ የሃዘን እንጉርጉሮ አንጎራጎረ።

ቁዘማ ስ 1. ሃዘን፡ ትካዜ። 2. ልቅሶ፡ የሃዘን እንጉርጉሮ።

ቆዘረ ግ ነፋ፥ ጎሰረ፡ ቀበተተ (ሆድን)።

ቁዝር ቅ ሆዱ ጉስር፡ ዝርጥጥ ያለ።

ቁዝር አለ ግ ሆዱ ጉስር፡ ቅብትት አለ፡ ተቆዘረ።

ተቆዘረ ግ ሆዱ ተቀበተተ፡ ተጎሰረ።

ቆየ ግ 1. ኖረ። *ለመቄው እዚህ አገር ብዙ ጊዜ ቆይቷል።* 2. ጠበቀ። *ቆየኝ እየመጣሁ ነው።* 3. ዘገየ፡ ጊዜ አሳለፈ። *በጣም ቆይቶ መጣ።*

የቆየ ቅ 1. ብዙ ጊዜ የሆነው፡ የሰነበተ። 2. የድሮ የጥንት፡ በፊት ጀምሮ የነበረ፥ የኖረ።

ቆይ [ብቻ] ዛቻን ለመግለፅ የሚያገለግል ቃል። *ቆይ እንዳሾፍክ ላትቀርም።*

መቆያ ስ በምሳና በእራት መካከል የሚበላ አነስተኛ መጠን ያለው ምግብ፡ መክሰስ፡ የእራት መዳረሻ።

ቆይታ ስ በአንድ ጉዳይ ላይ በምስጢር ለመምከር፥ ለመነጋገር የሚደረግ አጭር ስብሰባ (ብዙውን ጊዜ በተከበሩ ሰዎች መካከል)። 2. በአንድ ቦታ፥ አገር፥... ሆኖ የሚያልፍ ወይም የሚያሳልፉት የተወሰነ የጊዜ መጠን። *በናዝሬት ቆይታዬ ደስተኛ ነበርኩ።* 3. ከተወሰነ ሰው ጋር ወይም ከተወሰነ ቦታ ሆኖ የተወሰነ ጊዜ ማሳለፍ።

***ቆደሰ**

መቋደሻ ስ የድሮ ጨጓራ።

ተቋደሰ ግ 1. ተካፈለ፡ ተጋራ፡ ተቋረሰ። 2. ቀመሰ፥ አፉን አሟሸ።

አቋደሰ ግ1. አካፈለ፡ አጋራ፡ አቋረሰ። 2-. አቀመሰ፥ አስከፈ።

ቆዳ ስ 1. ከሰው ወይም ከማንኛው የእንስሳ ስጋ በስተላይ የሚገኝ የስጋ ሽፋን፡ ልባስ። 2. ከእንስሳ ስጋ ላይ የተገፈፈና ከስጋው ተለይቶ ለብቻው የተደረገ የስጋ ሽፋን፡ ቁርበት፡ አንጋሬ፥ ሌጦ። 3. የፍራፍሬ ሽፋን፡ ልጣጭ። 4. (ዘይ.) ነገር ቶሎ የማይገባው፡ ደደብ።

ቆዳ መሬት ስ ለምነት የሌለው፡ ቢዘሩበት የማያበቅል መጥፎ መሬት።

የቆዳ ስፋት ስ የአንድ ቦታ፡ ክልል፡ ሃገር፥... ጠቅላላ ስፋት።

የቆዳ በሽታ ስ በሰውነት ቆዳ ላይ የሚወጣ ማንኛውም አይነት ህመም (እከክ፡ ቁስል፥...)።

ቆጋ ግ 1. በጅራፍ ገረፈ፡ ሸንቆጠ፡ ቆነደደ። 2. የጅራፉን ጫፍ (ቁግን) አበጀ። 3. (ተራ.አነ.) ሸጠ።

ቁግ ስ የገመድ ጅራፍ ጫፍ(ስእሉን ጅራፍ ስር

ተመ.)።

ቁጊያም (ቊጋም) ቅ (ስድብ) ክሲታ።

ቆጠረ ግ 1. አንድ፣ ሁለት፣...እያለ የአንድን ነገር ብዛት ለይቶ አወቀ (በማስላት፣ በመክፈል ወይም ነገሮችን አንድ በአንድ በማሰብ፣ በማየት፣ በመንካት፣...)። 2. የቁጥሮችን ስም (1፣2፣3፣...) በየተራ ጠራ። 3. ጥቅም ላይ የዋለን የመብራት፣ የውሃ፣... መጠን፣ ልክ መዘገበ (ሰራተኛው ወይም ቆጣሪው)። 4.አዘጋጀ (ቅኔን)።

እንደ___ ቆጠረ እንደ___አየ፤ ተመለከተ። *እኔንም እንደ ሰው ቆጥረህ ቸርነትህን አደረግክልኝ ፈጣሪዬ?*

ከ___ ቆጠረ ከ ___መደበ። *እሱንም ከሰው ቆጠርከው?*

መቁጠሪያ ስ አንድን የፀሎት ቃል ስንት ጊዜ መላልሰው መጥራታቸውን ለማስታወስ ይረዳቸው ዘንድ ፀሎተኞች እንደ ዶቃ በክር ሰክተው የሚይዙት፤ ቅርፁ ድቡልቡል ሆኖ መጠኑ ዳቦ ቆሎ የሚያክል፤ ብዛቱ እንደየፀሎተኛው ፍላጎት የሚወሰን፣ ከእንጨት ወይም ከሌላ ነገር የሚዘጋጅ የፀሎት መገልገያ እቃ።

መቁጠሪያ ቁጥር ስ ከአንድ ጀምሮ ያሉ አሃዞ ቁጥሮች (1፣2፣3፣...)።

ቆጠራ ስ የገባውን፣ የወጣውንና በእጅ ላይ ያለውን ንብረት ለይቶ ለማወቅና ለመመዝገብ የሚደረግ እቃን የመቁጠር ተግባር፤ የንብረት ቆጠራም ይባላል።

ቆጣሪ ስ አገልግሎት ላይ የዋለን የመብራትና የውሃ መጠን በየጊዜው መዝግቦ የሚይዝ፤ ከውሃ ቧንቧው አፍ አጠገብ እንዲሁም ከመብራት መስመር መቀበያ ላይ የሚደረግ መሳሪያ።

የቆጣሪ [ግብር] ስ ጥቅም ላይ ከዋለ የውሃ ወይም የመብራት ፍጆታ ዋጋ ሌላ፣ ለቆጣሪው እቃ ተብሎ በግብር መልክ የሚከፈል ገንዘብ።

ቁጥር ስ 1. መጠን፣ ልክ፣ ብዛት። *የህዝቡ ቁጥር ምን ያህል ነው?* 2. መጠንን፣ ልክን፣ ብዛትን፣...የሚያሳይ ምልክት (እንደ 1፣2፣3፣...)። 3. እንደ መለያ የሚያገለግል አሃዝ። *ቁጥሩ___ የሆነ ሸሚዝ፤* 4. የአንድ ነገር የርዝመት፣ የስፋት፣... መጠን፣ ደረጃ። *የጫማህ ቁጥር ስንት ነው?* 5. ሂሳብ፣ ስሌት (የመደመር፣ የመቀነስ፣ የማባዛት፣ የማካፈል አሰራር፤ ትምህርት)።

በቁጥር ነው ጥቂት ነው። *ያላየኋቸው አገሮች በቁጥር ናቸው።*

በ___ ቁጥር በ___ጊዜ ሁሉ። *በመጣ ቁጥር ይጠይቀኛል።*

ከቁጥር አይገባም ትንሽ ነው፤ አይረባም፤ እንዳለም አይታሰብ።

ከቁጥር ወጣ 1. ተለየ፤ ተገለለ፤ ተባረረ፤ ተወገደ (ከማህበር፣ ከቡድን፣... አንድነት)። 2. እንደሰው ወይም እንደ ቁምነገር የሚያየው ታጣ፤ ጠፋ።

ቁጥጥር ስ የአንድን ነገር ሁኔታ የመከታተል፣ የመጠባበቅ፤ የመቆጣጠር ተግባር።

[በ፥ከ] ቁጥጥር ስር አዋለ /አደረገ በስልጣኑ፣ በፍላጎቱ፣ በትእዛዙ፣... ስር እንዲሆን አስገደደ።

ተቆጠረ ግ 1. ታሰበ፤ ተሰላ፤ ቁጥሩ ተነገረ፤ ታወቀ። 2. ታየ፣ ታሰበ፣ ተገመተ። *እንደ ስህተት ተቆጠረ።* 3. በነጥብ ተያዘ፣ ታሰበ። 4. ተዘረዘረ፤ ተነገረ። *ተቆጥሮም አያልቅ።*

ተቆጣጠረ ግ 1. ተከታተለ፣ ተጠባበቀ። 2. አንድን ነገር ወይም ቦታ በይዞታው ስር አደረገ በቁጥጥሩ፣ በፍላጎቱ ስር እንዲውል አስገደደ።

መቆጣጠሪያ ስ የአንድን ነገር ተግባር፣ እንቅስቃሴ፣ ሁኔታ፣... ለመከታተል፣ ለመቆጣጠር፣... የሚያስችል ዘዴ፣ መንገድ፣ መሳሪያ።

ተቆጣጣሪ ስ አንድ ተግባር በአግባቡ መፈጸሙን፣ ንብረት በአግባቡ መያዙን፣ ደንብና ስርአት በወጉ መጠበቁን የሚከታተል ሰው።

ተቋጠረ ግ ዘሩን ወይም ትውልዱን በመቁጠር የእነማን ወገን መሆኑን ለማስረዳት አንዱ ለሌላው ተናገረ፤ አወራ፤ እገሌን የወለደው እገሌ ነው እያለ የዘመዶቹን ስም በየተራ ጠራ።

የተቋጥሮ ዝምድና ስ የሩቅ ዝምድና፤ ዝምድናው እንደ አጎትና አክስት በጣም ቅርብ ያልሆነ የትውልድ ግንኙነት።

አቁጣሮ ስ በመቁጠሪያ አማካኝነት የሚደረግ ፀሎት።

አቆጣጠር ስ የቆጠራ፣ የስሌት መንገድ። *እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር/ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር።*

ቆጠበ ግ 1. ቶሎ እንዳያልቅ በጥንቃቄ ያዘ፣ ተጠቀመ፣ አጠቃቀሙን በጥቂቱ፣ በመጠኑ፣ በልኩ፣... አደረገ። 2. በየጊዜው ትንሽ ትንሽ በማስቀመጥ ገንዘብ አጠራቀመ።

ቁጠባ ስ ገንዘብን፣ ንብረትን፣... በአግባቡ በስነስርአቱ የመገልገል ወይም በመጠን በመጠኑ የመጠቀም ድርጊት።

የቁጠባ ሂሳብ ስ በየጊዜው ጥቂት በጥቂት ባንክ ውስጥ በማስቀመጥ የሚጠራቀምና ወለድ ሊያስገኝ የሚችል ገንዘብ።

የቁጠባ ቤት ስ በአነስተኛ ወጪ በመንግስት እቅድ የሚሰራ ቤት።

ቁጥብ ቅ ብዙ ከመናገር፣ ከማድረግ የታቀበ፤ ራሱን በራሱ የጠበቀ፤ የተቆጣጠረ።

ቆጣቢ ቅ ብዙ የማያጠፋ፤ የማያባክን

(ገንዘብን፥ ንብረትን፥...)።

ተቆጠበ ግ ተጠበቀ፡ ተወ፡ አንድን ነገር ከማድረግ፡ ከመፈፀም ራቀ፡ ራሱን ተቆጣጠረ።

ቆጠቆጠ^{1} ግ 1. አቃጠለ፡ ለበለበ፡ ፈጀ፡ የተላጠ ቁስል ውሃ ወይም ሌላ ነገር ሲነካው የሚሰማውን የህመም አይነት ስሜት ተሰማ። 2. (ዘይ.) አንገበገበ፡ ቆጨ፡ የቁጭት ስሜት ተሰማ።

ቆጠቆጠ^{2} ግ 1. የዛፍን ቅርንጫፍ፡ ክንፍ፡ ቅጥያ መለመለ። 2. ቁጥቋጦን፥ ቅጠላ ቅጠልን መነጠረ።

ቁጥቋጦ ስ 1. በተፈጥሮ ቁመናው እንደ ዛፍ ትልልቅ (ረጃጅም)፡ ወፍራም ያልሆነና እንደ ቀጋ፡ አጋም፡... ያለ የእፅዋት አይነት። 2. አዲስ በተቆረጠ የዛፍ ጉቶ ወይም ጉራጅ ላይ የሚበቅል የዛፍ ለጋ ቅጣይ፥ ቀንበጥ።

አቆጠቆጠ ግ አለመለመ፡ አፈጠፈጠ፡ አጎፈጎፈ።

***ቆጠቆጠ**^{1}

ቆጥቋጣ (ቆጠቆጥ) ቅ ገብጋባ፡ ስስታም፥ ቆንቋና።

ቁጥ ቁጥ ተው.ግ. የመቁናቆን፥ የስስት፥ የቆጣቢነት አድራጎት። *ሲሰጥ ሲጋብዝ ነው ቁጥቁጥ አያውቅም።*

ቁጥቁጥ አለ ግ ተስገበገበ፡ ሰሰተ፡ ተንቆጣቆጠ።

ተንቆጣቆጠ ግ ተስገበገበ፡ ሰሰተ፡ ቁጥቁጥ አለ።

አንቆጣቆጠ ግ አቁናቆነ፡ አሰሰተ።

***ቆጠቆጠ**^{2}

ተንቆጠቆጠ ግ አሸበረቀ፥ አጌጠ፥ አማረ፥ ተዋበ።

አንቆጠቆጠ ግ አሸበረቀ፥ አስጌጠ፥ አስዋበ።

እንቁጥቁጥ ቅ ያሸበረቀ፡ ያጌጠ።

ቆጠቆጥ "***ቆጠቆጠ**^{1}" ስር "**ቆጥቋጣ**" ን ተመ.

ቆጠጠ ግ 1. ኮሳ፥ ቀጣጥ ማለ። 2. ጎበበ፥ ቆበበ፡ ጉብ፡ ጉች ብሎ ታየ።

ቁጣጥ ስ በጣም ትንሽና ለስላሳ የሆነ የጨቅላ (ጥጃ፡ ግልገል፡ ልጅ) ኩስ።

ቁጢጥ አለ ግ ሙሉ በሙሉ ሳይሆን በእግሮቹ ጣቶች በቋፍ ሆኖ ተቀመጠ።

***ቆጣ**

ቁጡ ቅ ንዴተኛ፡ በትንሹ ነገር ሁሉ የሚበሳጭና ቶሎ የሚናደድ።

ቁጣ ስ 1. የንዴት የመበሳጨት፡ የመናደድ፡ ሃይለቃል የመናገር፡ የማኩረፍ አድራጎት። 2. ምክር አዘል ተግሳፅ፡ ዘለፋ። 3. (ዘይ.) መአት፡ መቅሰፍት፡ ውርጂብኝ።

ቆጣ አለ ግ ሲቀምሱት ጣእሙ ኮምጠጥ፥ ኮስተር፥ ዘለል አለ (ጠላ፡ ጠጅ፡ ቅቤ)።

ተቆጣ ግ 1. ተናደደ፥ ተበሳጨ፡ በቁጣ ስሜት ተናገረ። 2. ተቀየመ፡ አኩረፈ። 3. ምክር አዘል በሆነ አነጋገር ገሰፀ፡ ሰደበ፡ ዘለፈ (አባት ልጁን፡ ታላቅ ታናሹን፥...)። 4. ቆጣ አለ። 5. በተለያየ ምክንያት ሰውነት ወይም ገላ አበጠ፥ ተጉረበረበ፥...።

ተቆጪ ስ መካሪ፡ ተቆጣጣሪ። *ተቆጪ የሌላቸው ልጆች መጨረሻቸው ላያምር ይችላል።*

ተቆጣጣ ግ መከረ፡ መካከረ። *የተጣሉትን ልጆች ተቆጣጥቶ አስታረቃቸው።*

አስቆጣ ግ 1. አናደደ፡ አበሳጨ። 2. ቁጣ እንዲደርስበት፥ እንዲቆጡት አደረገ። 3. አስቀየመ፡ አስኮረፈ። 4. እንዲቆጣ አደረገ።

ቆጣሪ "**ቆጠረ**" ስር ተመ.

ቆጣቢ "**ቆጠበ**" ስር ተመ.

ቆጥ ስ አራት እግሩ መሬት ውስጥ የተተከለና ከፍታው ረጅም የሆነ የእንጨት አልጋ (ብዙውን ጊዜ በገጠር ገበሬዎች ቤት የሚገኝ)።

ቆጣስር (ቆጥ አስር) ስ ሚስት ያጨ ወንድ ልጅ የጋብቻቸው ወግ ተጠናቆ ጎጆ ከመውጣታቸው በፊት ከሚስቱ ወላጆች ዘንድ ተቀምጦ ለተወሰኑ አመታት እነርሱን ያገለግልበት የነበረ ጥንታዊ የጋብቻ ውል አይነት፡ ደንብ ወይም ስርአት።

ቆጥቋጣ "***ቆጠቆጠ**^{1}" ስር ተመ.

ቆጨ ግ ከነከነ፡ ቅሬታ አሳደረ፡ ፀፀተ።

ቁጭት ስ 1. ፀፀት፥ ንዴት፥ መቆርቆር። 2. ቂም፡ ቁርሾ። *አጋጣሚ ጠብቆ ቁጭቱን ተወጣ።*

ቁጭቱን ተወጣ አስቀይሞት ወይም አናዶት የነበረውን በመበቀል ረካ፡ ንዴቱን አበረደ።

ተቆጨ ግ ቅር ተሰኘ፡ ተናደደ፥ ተቆረቆረ፡ ተፀፀተ።

አስቆጨ ግ አስፀፀተ፡ ቅር አሰኘ፡ አናደደ።

***ቆጨቆጨ**

ቆጭቋጫ ቅ ነጭናጫ፡ ብስጩ።

ተንቆጫቆጨ ግ ተነጫነጨ፥ ተበሳጨ።

አንቆጫቆጨ ግ አነጫነጨ፡ አበሳጨ።

ቆፈረ ግ 1.ማሰ፡ ጎደፈረ፡ ጫረ (መሬትን)። 2.(ዘይ.) ጎረጎረ፡ ፈለፈለ፡ መረመረ (የተደበቀ ነገርን ለማግኘት፡ ለማውጣት)።

መቆፈሪያ ስ እንደ ዶማ፡ ድጅኖ፥ አንካሴ፥... ያለ መሬትን የመማሻ መሳሪያ።

ቁፋሮ ስ 1. በዶማ አማካይነት መሬትን የማረስ፡ የመጎድፈር ድርጊት። 2. በዶማ

አማካይነት የተቆፈረ መሬት።

ቆፋሪ ቅ 1. በዶማ መሬትን የሚነድፍር፣ የሚያርስ። ስ 2. ዶመኛ፤ መሬትን ለማረስ ለመጫር በዶማ የሚገለገል ሰው።

ቁፍርፍር አለ ግ ተቆፋፈረ።

ተቆፈረ ግ ተማሰ፤ ተነደፈረ፤ ተጫረ፤ በዶማ ታረሰ።

ተቆፋፈረ ግ ፈሳሰሰ፤ እዚህም እዚያም ተማሰ፤ በዶማ ታረሰ።

ቆፈነነ ግ እጅንና እግርን ያዘ፤ ላንቀሳቅስ አለ፤ አደነዘዘ (ብርድ)።

ቆፈን ስ እጅንና እግርን የሚይዝ፤ የሚያደነዝዝ ብርድ፤ ቅዝቃዜ።

ቆፈናም ቅ 1. በጣም ብርዳም ወይም ቀዝቃዛ የሆነ (ቦታ)። 2. (ስድብ) ሰውነቱ በቆፈን የደነዘዘ፤ ከርፋፋ። 3. (ዘይ.) ስስታም፤ ሲሰጥ እጁ በሰስት የሚንቀጠቀጥ።

***ቆፈጠነ**

ቆፍጣና ቅ ንቁ፤ ቀልጣፋ፤ ኩሩ።

ቆፋሪ "ቆፈረ" ስር ተመ.

ቆፍ

ቆፍ ቆፍ አደረገ ግ የመቆርቆር፤ የማንኳኳት፤ የመምታት አይነት ድምፅ አሰማ።

ቆፍጣና "*ቆፈጠነ" ስር ተመ.

ቋ^1 የ "ቀ" ፊደል ፍንዕቅ ዘር።

ቋ^2

ቋ አለ ግ ቀጭ፤ ኳ አለ፤ የመሰበር፤ የመገጨት አይነት ድምፅ አሰማ።

ቋሊማ ስ የተከተፈን ስጋ በቅመም አጣፍጦ በታሰበ ወተት አንጀት ውስጥ በመከተት የሚዘጋጅ የምግብ አይነት።

ቋመጠ ግ ጎመጀ፤ ጓጓ፤ ከጀለ (አንድን ነገር ለማየት፤ ለማድረግ፤ ለማግኘት)።

አቋመጠ ግ አጎመጀ፤ አጓጓ።

ቋሚ "ቆመ" ስር ተመ.

ቋር ስ በእንጨት አካል ላይ ተድቦልቡሎ ወይም አትሮ የሚታይ የእንጨት ጉጥ።

ቋራም ቅ ቋር ያለበት (እንጨት)።

ቋርፍ ስ ብዙውን ጊዜ መናኞች የሚመገቡት ከዱር እፅዋት ፍራፍሬና ስራስር የሚዘጋጅ የምግብ አይነት።

ቋሮ ስ ራስ ትልቅ አሳ።

ቋቁቻ ስ ብዙውን ጊዜ በሰው ፊት፤ አንገት፤ ደረት ላይ የሚወጣ የቆዳ በሽታ አይነት።

ቋቅ

ቋቅ አለ ግ 1. አስመለሰ፤ አስታወከ። 2. (ዘይ.) ሰለቸ፤ አስጠላ። *ስራው አስቸጋሪ ከመሆኑ የተነሳ ቋቅ አለው።*

ቋቅ እስኪለው እስኪያንገሸግሸው፤ እስኪሰለቸው።

ቋቋ

ቋቋቴ ስ የፍሬ መያዣውን ከረጢት በጣም አጣብቀው ሲጫኑት ከረጢቱ የፍንዳታ ድምፅ በማሰማት የሚተረተር የእፅዋት አይነት።

ቋ ቋ አለ ግ ተንቋቋ።

ተንቋቋ ግ 1. ቋቋ የሚል የድምፅ አይነት አሰማ። 2. በጣም ከማርጀቱና ሰውነቱ ከመሟረሩ የተነሳ በሚንቀሳቀስበት ጊዜ ሰውነቱ ቋቋ የሚል ድምፅ አሰማ።

አንቋቋ ግ ቋቋ የሚል የድምፅ አይነት አሰማ ወይም እንዲሰማ አደረገ።

ቋተ ግ አንድ ቦታ ላይ ተጠራቀመ፤ ተከማቸ (ለምሳሌ ፍሳሽ ውሃ)።

ቋት ስ 1. እህል ሲከካም ሆነ ወይንም ሲፈጭ ከወፍጮው ላይ የሚወርደው ክክ ወይም ዱቄት የሚከማችበት፤ ከባህላዊው የቀም ወፍጮ ጋር ተያይዞ ከጭቃ ወይም ከሸክላ የሚሰራ ማጠራቀሚያ። 2. መጠራቀሚያ፤ መከማቻ። *ሰውየው የበሽታ ቋት ነው።* (ዘይ.) ሆድ። *ቀን ከሌት የሚሰራው ቋቱን ለመሙላት ነው።*

ቋቱ ጠብ አይልም 1. አይጠራቀምም። 2. አይሟላም፤ አይሳካም።

ከቋት ከቋቱ ከስር ከስሩ፤ ወዲያው ወዲያው፤ ሳይቆይ።

አቋተ ግ 1. የሚፈጨውን እህል ከወፍጮው አናት አካባቢ አደረገ፤ ወይም የሚፈጨውን እህል በወፍጮው ማቋቻ ላይ ደቀነ። 2. አንድ ቦታ ላይ ተከማቸ፤ ከተረ (በመፍሰስ ላይ ያለ ፈሳሽ ነገር)።

ማቋቻ ስ የሚፈጨው እህል የሚቀመጥበት (የሚደቀንበት) የወፍጮው የላይኛው ጠርዝ፤ ወይም አናቱ።

ቋንቁራ ስ መንገደኛ የሚሸከመው ቅራቅንቦ፤ ሰባራ ሰንጥቁ፤ ጥቃቅን እቃ ሁሉ ባንድ ላይ (ቅሉ፤ አገልግሉ፤...)።

ቋንቋ ስ 1. ሰዎች እርስ በርስ ለመግባቢያነት የሚገለገሉበት፤ ሃሳባቸውን፤ ስሜታቸውን የሚገልፁበት፤ ስርአት ያለው የድምፆች የቃላት፤... ጥንቅር። 2. የአንድ ቡድን፤ ሃገር፤ ብሄረሰብ፤... አባላት ለመግባቢያነት የሚገለገሉበት የቋንቋ ቅርፅ ወይም አይነት። *የኔም ቋንቋ /አማርኛ ቋንቋ/ የአፍ መፍቻ ቋንቋ።* 3. የአገላለፅ መንገድ። *ሃሳቡን ተውና ቋንቋውን ብቻ አርምልኝ/ ገንዘቡን እንደማይከፍል በሚያሻማ ቋንቋ ነገራቸው።* 4.

የተወሰነ የህዝብ ክፍል እርስ በርስ ለመግባባት የሚገለገልበት ቃል ወይም ሃረግ፣...። *የአራዳ ቋንቋ /የሌቦች ቋንቋ።*

ቋንገር "ቋንጃ" ን ተመ.

ቋንዶ [ሃረግ] ስ ጠንካራ የሃረግ አይነት።

ቋንጃ (ቋንገር) ስ ከጉልበት በስተሂዋላ በባትና በጭን መካከል የሚገኝ መታጠፊያው ክፍል(ስእሉን በሰውነት ስር ተመ.)።

ቋንጃ ቆራጭ ስ የሰው ሃብትና ንብረት የሚዘርፍ፣ በሰዎች ላይ ግፍ የሚፈፅም፣ ወንጀለኛ፣ ሽፍታ፣ ወንበዴ።

ቋንጣ^1 ስ 1. በቀጭኑ ተዘልዝሎና ገመድ ወይም ሽቦ ላይ ተሰቅሎ እንዲደርቅ የሚደረግ የእንስሳት ስጋ። 2.ስ የበሰለና የደረቀ የበለስ ወይም የዋርካ ፍሬ። 3.(ዘይ.) ከሲታ ወይም በጣም ቀጭን የሆነ (ሰው)።

ቋንጣ እግር እግረ ቀጭን የሆነ (ሰው)።

ቋንጤ ወንበር ስ በጠፍር የተሰራና መደገፊያ ያለው የእንጨት ወንበር።

ቋንጣ^2 ስ በእንዝርት አናት ላይ የሚሰካ፣ ቆላፋ የሆነ ቀጭን ሽቦ።

ቋኛት ስ ከሃረግ ወይም ከመቃ የሚሰራ የአሳ መያዣ ሞላላ ቅርጫት።

ቋዝመን ስ እንደ ጩቤ ያለ አነስተኛ ካራ።

ቋያ ስ የደረቀና ያልታጨደ የበረሃ ሳር።

የቋያ እሳት ስ በቋያ ላይ የሚነሳና ከፍተኛ የመቀጣጠል ፍጥነት ያለው የሰደድ እሳት።

ቋድ ስ እንደዛብ አራት ማእዘንነት ያለው የሃር፣ የጠፍር፣... ጉንጉን።

ቋጠረ ግ 1. አንዱን ከሌላው ጋር አያያዘ፣ አቆራኘ፣ አጠላለፈ (ለምሳሌ አንድን ገመድ ከሌላ ገመድ ወይም ከሌላ ነገር ጋር)። 2. በጨርቅ ወይም በሌላ በተመሳሳይ ነገር ጠቅልሎ፣ ሸፍኖ አሰረ። *እረኛው ምሳውን በልብሱ ቋጥሮ ሄደ /ሴትዮዋ ሳንቲሞቹን በመሃረብ ቋጥራ አስቀመጠች።* 3. በውስጡ ያዘ፣ አዘለ፣ አቆረ። *የእሳት ነበልባል የገረፈው ገላው ውሃ ቋጠረ።* 4. አፍኖ ያዘ፣ ተቆጣጠረ። *ከስብሰባ ላይ ተነስቶ መውጣት ስለፈራ ሽንቱን ቋጥሮ ዋለ።* 5. አጠራቀመ፣ አካበተ፣ አኖረ። *ትንሽ ጊዜ ነግዶ ደህና ገንዘብ ቋጥሯል።* 6. አሴረ፣ ተበተበ (ነገርን)።

ቋጠረች በነሰች፣ አረገዘች።

መቋጠሪያ ስ 1. ማሰሪያ (ገመድ)። 2.መክተቻ፣ መያዣ፣ መጠቅለያ (ከረጢት፣ ስልቻ፣ ጨርቅ፣...)።

መቋጠሪያው ተበጥሷል ፈሱን መያዝ፣ ወይም መቆጣጠር አይችልም፣ በመጣበት ጊዜ ሁሉ ይፈሳል።

ቋጥር ስ እስር። *ቋጥሩ የጠበቀ ነው/ አይፈታም።*

ቋጥርጥር ቅ 1. እርስ በርሱ የተያያዘ፣ የተሳሰረ (ነገር)። *ፀጉሩ ቋጥርጥር ብሏል/ ተበጥሮም አያውቅ።* 2. ብዛት ያለውና ተቋጥሮ ተቋጥሮ የተቀመጠ እቃ። *ሴትዮዋ የገዛችውን ቅመማ ቅመም ለያይታ ከቋጠረች በኋላ ቋጥርጥሩን በአንድነት ተሸክማ ሄደች።*

ቋጥርጥር አለ ግ እርስ በርስ ተጠላለፈ፣ ተያያዘ፣ ተተባተበ፣ ተወሳሰበ።

ቋጠሮ ስ 1.እስር (የገመድ፣ የጨርቅ፣...)። 2. የተቋጠረ።

ተቋጠረ ግ 1. ታሰረ። 2. አብሮ ሆነ፣ አልነጠል አለ። 3. ደደረ፣ ጓጎለ።

ተቋጣጠረ ግ እርስ በርስ ተጠላለፈ፣ ተተባተበ፣ ተወሳሰበ።

ቋጥኝ ስ መጠኑ በጣም ትልቅ የሆነና መሬት ላይ ጉብ ብሎ የሚገኝ ድንጋይ።

ቋጨ ግ 1. የነጠላን፣ የጋቢን፣...ጫፍ ወይም ዘርፍ ገመደ፣ አከረረ፣ ፈተለ። 2. (ዘይ.) አንድን ሃሳብ፣ነገር፣ ጉዳይ፣... ከውሳኔ ወይም ከውጤት ላይ አደረሰ፣ አጠቃለለ፣ ደመደመ።

ቁጨት ስ 1. የነጠላን፣ የጋቢን፣...ጫፍ ወይም ዘርፍ የመገመድ፣ የማክረር ወይም የመፍተል ተግባር። 2. የተገመደ ወይም የተፈተለ የነጠላ፣ የጋቢ፣... ጫፍ ወይም ዘርፍ።

ቋጨራ ስ ለቤት ክዳን ስራ እንዲያመች በገብስ ነዶ መጠን የሚታሰር ሰንበሌጥ፣ ጓሳ፣...።

ቋጫ ስ ከስንደዶ ወይም ከአክርማ የሚሰፋ የወተት ማለቢያ፣ ጮጮ።

***ቋፈ**^{1}

ቋፍ ስ ጫፍ፣ ጠርዝ፣ አፋፍ። *ቋፍ ላይ አትቀመጥ፣ ትወድቃለህ።*

በቋፍ [ላይ] ነው ትንሽ ሰበብ፣ ምክንያት ይበቃዋል (አንድ ነገር ለመሆን፣ ለማድረግ፣...)።

***ቋፈ**^{2}

ተቋፈ ግ ተቆነነ፣ ተጀነነ (በአካሄድ፣ በአነጋገር፣...)።

አቋፈ ግ ቆነነ፣ ጀነነ፣ ቀስ አደረገ።

አስቋፈ ዝ.ክ.

በ

በ ከ "ቀ" ፊደል ዘር ቀጥሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል (ግእዙ ሆሄ)::

በ^{1}___ 1.በስም መነሻ ላይ እየተቀጠለ ማድረጊያነትን የሚያመለክት ምእላድ:: *ተማሪው በብእር ይፅፋል*:: 2. ተውሳከ ግሳዊ አገልግሎት የሚሰጥ ወይም የድርጊት ሁኔታን ለማመልከት የሚያገለግል ምእላድ:: *በአስቸኳይ /በዝግታ/ ቀስ በቀስ*: 3. ቦታን፣ አቀማመጥን፣ ጊዜን፣... ከሚያመለክቱ ቃላት ጋር እየተጣመረ መስተዋድዳዊ ሃረግን የሚመሰርት ምእላድ:: *በጠረጴዛው ላይ /በወንዙ አጠገብ/ በቀኝ በኩል/ በዛሬው እለት*::

በ^{2}___ "ብ___"ን ተመ.

በ^{3}___ "ከ___"ን ተመ.

በሃ "ቡሃ"ን ተመ.

በሃ በግ "ቡሃ" ስር "ቡሃ በግ"ን ተመ.

በሃ (ብሃ)ድንጋይ ስ በቀላሉ ፍርክስክስ የሚል ነጣ ያለ የድንጋይ አይነት፣ ብክክ እየተባለም ይጠራል::

በሀረ ሉሚ "*በከረ" ስር "በኩረ ሉሚ"ን ተመ.

በሀር "*በከረ" ስር "በኩር"ን ተመ.

በለለ ግ 1. ተበላሸ፣ ጠፋ፣ መና ቀረ:: 2. ተሞላቀቀ፣ ቀበጠ፣ ጠባዩ ብልሹ ሆነ:: 3. በነነ፣ በረረ::

ብሉል ቅ ከንቱ፣ መና፣ ብልሹ::

በለሴ ስ በወፍራሙ የተፈተለ፣ ሻካራና ዘክዛካ የሆነ የሸማ አይነት::

በለስ ስ 1. አዳምና ሄዋን በገነት ሳሉ የፈጣሪን ትእዛዝ ጥሰው ፍሬዋን ስለበሉ የተረገመችው ዛፍ እንደሆነች የሚነገርላት በገነት የምትገኝ ዛፍ ስም:: 2. ቅጠሉ ነጣ ብሎ ሰፋ ያለ፣ ነጭ ፈሳሽ የሚወጣው የእፅዋት አይነት፣ ከዚሁ እፀዋት የሚገኘው ፍሬም በለስ ይባላል::

በለስ ቀናው / አገኘ 1.አደን ሄዶ የሚፈልገውን ገድሉ ተመለሰ:: 2.ተሳካለት፣ ሆነለት፣ ጥሩ እድል አጋጠመው::

***በለሸ**

ብላሽ ቅ 1. የማይረባ፣ ከንቱ፣ ለቁም ነገር የማይሆን:: 2. ነፃ:: *ይህን ልብስ በብላሽ ሰጠኝ*::

ብልሹ ቅ የማይረባ፣ ከንቱ፣ ለቁም ነገር የማይሆን::

ብልሽት ስ እክል፣ ሳንካ፣ ጉድለት:: *ሊቃው ብልሽት ለለው*::

ብልሽት አለ ግ ተበላሸ::

ብልሽትሽት አለ ግ 1.ፈፅሞ የተበላሸ፣ ጥቅም የማይሰጥ ሆነ::2. አመሉ፣ ጠባዩ መጥፎ ሆነ::

ተበላሸ ግ 1. አደፈ፣ ቆሸሸ:: 2. ተሰናከለ፣ እክል አጋጠመው:: *መኪናው ተበላሸ*: 3. ጠባዩ መጥፎ ሆነ:: 4. ከንቱ፣ የማይረባ፣ የማይጠቅም ሆነ:: 5.ያለጊዜው፣ ያለአግባብ ሞተ:: *ያንን የመሰለ ጀግና ተበላሸ*::

አበላሸ ግ 1. አጎደፈ፣ አቆሸሸ:: 2. አሰናከለ፣ የማይሰራ እንዲሆን አደረገ:: 3. ጠባየ መጥፎ አደረገ:: 4.ከንቱ፣ የማይረባ፣ የማይጠቅም አደረገ::5.ያለጊዜውና ያለአግባብ ገደለ፣ አጠፋ::

በለቀጠ ግ ሙሉ በሙሉ ከፈተ፣ በረገደ::

ብልቃጥ ቅ (ነውር፣ ስድብ) 1. ሃፍረተ ስጋዋ እንዳይታይባት ጥንቃቄ የማታደርግ፣ በርጋጅ:: 2. ስነስርአት የሌላት፣ የሰው አይን የማትፈራ፣ መንቃራ::

ተበለቀጠ ግ ተከፈተ፣ ተበረገደ::

ተበላቀጠ ግ ስነ ስርአት አጣ፣ ተመናቀረ::

***በለበለ**

ነበልባል ስ 1.የነደደ እሳት ጫፍ፣ ላንቃ፣ ልሳን:: 2. (ዘይ.) ለፍላፊ፣ ምላሰኛ::

ተንበለበለ ግ 1.በሃይል ነደደ፣ ተንቀለቀለ፣ ተንቦገቦገ:: 2.(ዘይ.) በፍጥነት ተናገረ፣ ለፈለፈ::

አንበለበለ ግ 1. በሃይል አነደደ፣ አንቀለቀለ፣ አንቦገቦገ:: 2. (ዘይ.) ያለ ምንም ችግር በፍጥነት አነበበ::

በለተ ግ ታርዶ ቆዳው የተገፈፈን እንስሳ አካል በመልክ በመልኩ እየለየ ቆረጠ፣ ገነጠለ፣ ከፈለ፣ ብልት አወጣ::

መበለቻ ስ ብልት ለማውጣት የሚያገለግል ቢላዋ፣ ካራ::

በላች ቅ ከብት አርዶ፣ ቆዳውን ገፎ፣ ብልቱን በየመልኩ እየለየና እየቆረጠ የማውጣት ሙያ ያለው፣ አራጅ፣ ብልት አውጪ::

ብልት ስ 1. እንደ ሽንጥ፣ እግር፣...ያሉና ከዋናው አካል ተለይቶ ሊታወቅና ለብቻው ተነጥሎ ወይም ተቆርጦ ሊወጣ የሚችል ክፍለ ስጋ፣ አካል:: 2.ሃፍረተ ስጋ:: 3.(ዘይ.) ስልት:: *የነገር ብልት ማወቅ ጠቃሚ ነው*::

ብልት አወጣ የታረደ እንስሳን አካል በየብልቱ እየለየ ቆረጠ፣ እግሩን፣ ሽንጡን፣...እየቆራረጠ ለየብቻ አደረገ::

ብልት አውጪ ስ የታረደ የእንስሳን አካል በየክፍሉ ለያይቶ የመቁረጥ ችሎታ ያለው፣ በላች::

በለተተ ግ አረጀ፤ ሸመገለ።

ባልቴት ቅ 1. አሮጊት። ስ 2. ልባም፡ ባለሙያ ሴት።

በለዘ ግ 1. በአደጋ ወይም በሌላ ምክንያት የቀድሞ መልኩ ተለወጠ፥ ጠቆረ፥ ዘነነ። 2. ቸከ፥ አደፈ፥ ልማም ያዘ(ጥርስ)።

ብልዝ ቅ 1. የጠቆረ፥ የበለዘ። 2. የቸከ፥ ልማም የያዘ (ጥርስ)።

በለገ ግ 1. በበልግ ወራት ለበልግ የሚበቃ ዝናም ዘነመ። 2. የበልጉ አዝመራ ሰመረ፡ አማረ።

በልግ(ብላጊ) ስ ለአዝመራና ለግጦሽ ሳር በቂ የሚሆን የበጋ ዝናም የሚገኝበት ወቅት (በአብዛኛው ከየካቲት እስከ ሚያዝያ ያሉት ወራት)።

በልግ ሰጠ በለገ፤ በልግ ሆነ።

የበልግ እህል ስ በበልግ ወቅት ተዘርቶ የሚሰበሰብ አዝመራ።

የበልግ ዝናም ስ በበልግ ወቅት የሚጥል ዝናብ።

አበለገ ግ የበልግ ዝናም ጣለ፡ በልግ ሆነ።

በለጠ[1] ግ 1. (በርዝመት፡ በክብደት፡...) ከሌላው ላቀ፥ ከፍ አለ። 2. ከሌላው ተሻለ።

በበለጠ(በይበልጥ) በተሻለ፡ በአብዛኛው።

ብልጫ ስ ከፍታ፥ ትልቅነት።

ተበለጠ ግ 1. ከሌላው አነሰ፡ የበታች ሆነ። 2. ተሸነፈ። 3. ተሞኘ፡ ተታለለ።

ተባለጠ ግ እኩል አልሆን አለ፥ አንዱ ከሌላው አነሰ ወይም ላቀ፤ ተዛነፈ።

ተባለጥ ስ እኩል አለመሆን፤ ተዛነፍ።

ተበላለጠ ግ 1. አለመጣጠን ወይም እኩል አልሆን አለ፡ ተዛነፈ። 2. አንዱ ከሌላው ጋር በቁመት ተለካካ፡ ተወዳደረ።

አበለጠ ግ አላቀ፡ ከፍ አደረገ።

አበላለጠ ግ 1. አዛነፈ፥ አንዱን ከፍ ሌላውን ዝቅ አደረገ። 2. አወዳደረ፡ አንዱን ከሌላው ጋር አነፃፀረ (የሚልቀውን፡ የተሻለውን ለማወቅ)። 3. አዳላ።

አባለጠ ግ አበላለጠ።

አስበለጠ ግ 1. ከሌላው አላቀ፡ ከፍ አደረገ። 2. በሌላው እንዲበለጥ አደረገ።

በለጠ[2] ግ በአስተሳሰብ፡ በእውቀት፥...ከሌላው ላቀ፥ ከፍ አለ።

ብልጥ ቅ 1.ብልህ፥ አዋቂ። 2. ጮሌ፡ አራዳ።

ብልጣብልጥ ቅ ጮሌነት የሚያበዛ።

ብልጠት ስ 1. ብልሃት፡ ዘዴ። 2.ጮሌነት።

ተብለጠለጠ ግ 1.ተትከረከረ፡ ተጋ፡ ተጣጠረ። 2. ብልጠት፡ ጮሌነት አበዛ።

ተብለጥላጭ ቅ 1. ትጉህ፡ ታታሪ። 2. ጮሌ።

አብለጠለጠ ግ 1. አተጋ፡ አትከረከረ። 2. ብልጣብልጥ አደረገ።

በለጠገ "በለፀገ" ን ተመ.

በለጠጠ ግ ያለወጉ፥ ያለቅጥ በጣም አድርጎ ከፈተ፥ ገለጠ (አይንን፥ መዝጊያን፡...)።

በልጣጣ(በለጠጥ) ቅ (ዘይ) 1.ሃፍረተቢስ፥ የሰው አይን የማይፈራ። 2. ቀበጥ፡ ምልፋጭ፡ እዩኝ እዩኝ ባይ።

ብልጥጥ አለ ግ ተበለጠጠ።

ተበለጠጠ ግ ያለወጉ፡ ያለአግባቡ በጣም ተገለጠ፥ ተከፈተ (አይን፥ መዝጊያ፡...)።

ተንበላጠጠ ግ 1. በማስፈራራት መልክ አይኑን አፍጥጦ ወዲያና ወዲህ መላልሶ ተመለከተ። 2. እዩኝ እዩኝ የሚል አይነት አድራጎት አሳየ። 3. (ዘይ) ቀበጠ፥ ተሞላፈጠ።

አንበላጠጠ ግ በማስፈራራት መልክ አይኑን ያለ ቅጥ ገልጦ ወይም አፍጥጦ ወዲያ ወዲህ አየ፥ ተመለከተ።

***በለጨ**

በለጭ ስ ብልጭልጭነት ያለው የድንጋይ አይነት፡ በረቦጭ።

በለጭማ ቅ ግንባሩ ላይ ነጭ የሆነ (እንስሳ)።

ብልጭታ ስ ቦግታ፡ ድንገት ታይቶ የሚጠፋ የብርሃን ነፀብራቅ።

ብልጭልጭ ቅ 1. የሚያብረቀርቅ፥ የሚያንፀባርቅ፥ ቦግቦግ የሚል። 2. (ዘይ) ሲያዩት ለጊዜው አይን የሚስብ፡ ደስ የሚል ግን በጣም ጊዜያዊና ተራ የሆነ፡ መናኛ (እቃ፡ ጌጥ፡...)።

ብልጭልጭታ ስ ነፀብራቅ፡ ብርቅርቅታ (የመብረቅ፡ የመስታወት፡...)።

ብልጭልጭ አለ ግ አብለጨለጨ።

ብልጭ አለ ግ ድንገት ቦግ አለ፡ በራ።

ብልጭ አለለት ድንገት ታየው፡ ትዝ አለው፡ ተከሰተለት(ሃሳብ)።

ብልጭ አለበት የሚያናድድ፥ የሚያስቆጣ ነገር ድንገት ተሰማው።

ብልጭ ድርግም አለ ብርት፡ ጥፍት፡ ጥርኝ ብርኝ አለ።

ብልጭ አደረገ ግ 1. አበራ፡ አነደደ

(በጥቂቱ)። 2. ጥቂት ፍንጭ ሰጠ (ለሃሳብ)።

ተብለጨለጨ ግ 1.ተንፀባረቀ፡ ተብረቀረቀ። 2. ተጊያጊያጠ፡ ተሽቀረቀረ፡ አሸበረቀ።

አብለጨለጨ ግ አንፀባረቀ፡ አብረቀረቀ። 2. ተጊያጊያጠ፡ ተሽቀረቀረ፡ አሸበረቀ።

በለፀገ(በለጠገ) ግ ከበረ፡ ሃብት አገኘ።

ባለፀጋ(ባለጠጋ) ስ ሃብታም፡ ከበርቴ፡ ባለገንዘብ።

ብልፅግና ስ ሃብታምነት፡ የኢኮኖሚ እድገት።

አበለፀገ ግ 1. ባለፀጋ፡ ሃብታም አደረገ። 2. አዳበረ፡ አሳደገ።

በላ ግ 1. ተመገበ። 2. አሳመጠ፡ አኘከ። 3.ነከሰ። *ውሻ እንዳይበላህ ተጠንቀቅ*። 4. አሳከከ፡ ቆጠቆጠ። 5.አሸነፈ፡ ረታ፡ ገቢ አገኘ (በቁማር)። 6. ጨረሰ፡ ፈጀ። *መኪናዋ ብዙ ነዳጅ ትበላለች*።7.ተቀበለ፡ወሰደ። *ጉቦ በላ*። 8.አቃጠለ፡ ፈጀ። *እሳት በላው*።

ሲበሉ የላኩት 1. የተላከውን መልእክት (ቃል) የሚረሳ፡ የሚዘነጋ። 2. ችኩል፡ ወደመጣበት ለመመለስ የሚጣደፍ።

እበላ ባይ የግል ጥቅም ለማግኘት ሲል ሌላውን ለመምሰል የሚሞክር፡ ለጥቅም ሲል ከሌላው ጋር የሚተባበር፡ አስመሳይ፡ አጎብዳጅ።

የበላበትን ወጪት ሰባሪ ውለታ ቢስ፡ መልካም ላደረገለት ክፉ የሚመልስ።

የብላ ተባላ ዘመን መተሳሰብ፡ መተዛዘን የሌለበት፡ የግል ጥቅም፡ ፍላጎት ሰውን እርስበርሱ የሚያናቁርበት፡...ጊዜ።

ይብላኝ (ይብላኝለት) ሃዘንን፡ ትዝብትን የሚገልፅ ቃል። *ይብላኝ ይህንን የመሰለ ልጅ የሚያስጠጋው አጥቶ ከበረንዳ ያድራል / ለእርሱ ይብላኝ እንጂ እኔስ እንዳማሁ አልቀርም*።

መብል ስ ምግብ፡ የሚበላ ነገር።

በሊታ ቅ ያገኘውን ሁሉ የሚበላ፡ ሆዳም።

በላተኛ ስ 1. በአንድ የቤተሰብ ሃላፊ ስር የሚተዳደር ሰው፡ ተቀላቢ። 2. ተመጋቢ፡ ምግብ ፈላጊ። ቅ 3. ብዙ የሚበላ፡ ሆዳም።

-በል(-በላ፥ -በሌ) 1.(በቦዝ አንቀፅ ከሚነገር ግስ ጋር የሚጣመር ከፊል ቃል) ቀደም ሲል የተጠቀሰውን ስራ እያከሄደ የሚኖር፡ የሚተዳደር። *አርሶ በል*። 2. (ከስም ጋር የሚጣመር ከፊል ቃል) ቀደም ሲል የተጠቀሰውን ነገር የሚበላ ወይም ዘውትር የሚመገብ። *ሳር በል እንስሳ*።

ብላቶ ስ 1.ፍሬው ከተበላ በኋላ የሚቀረው የእህል ገለባ፡ የፍሬው ሽፋን፡ ጥርጣሬ፡ ትርፍራፊ። 2. የአገዳ ምጣጭ። 3. አውሬ ያስተረፈው ቅንጥብጣቢ ስጋና ቆዳ። 4. በፈንጣጣ፡ በቂጥኝ፡... ቁስል ምክንያት ከሰውነት ላይ የሚቀር ጠባሳ።

ብሉት(ብልት) ስ የፍስክ ቀን።

በላ በላ አደረገ ቶሎ ቶሎ ተመገበ፡ ፈጠን ፈጠን እያለ በላ።

ተበላ ግ 1. አለቀ፡ ሳሳ። *ሱሪው ጉልበቱ ላይ ተበልቷል*። 2. ተረታ፡ ተሸነፈ። 3. ተገደለ።

ተባላ ግ 1.እርስ በርስ በነገር ተናቆረ፡ ተራኮተ፡ ተጋጨ፡ ተጣላ፡ስምምነት አጣ። 2.በጣም አዘነ፡ አነባ፡ ተላቀሰ (ብዙ ሰው)። 3.ተገዳደለ፡ ተጨራረሰ፡ ተበላላ።

ተብላላ ግ 1.ተዋሃደ፡ ተሟሟቀ፡ ፈላ (ድፍድፍ)። 2. ተውጠነጠነ፡ ታሰበበት፡ ተመከረበት(ሃሳብ)። 3. የ"**ተባላ**"ን ሶስተኛ ፍቺ ተመ.

አበላ ግ 1.መገበ። 2.ሰጠ። *ጉቦ ሳያበሉት ጉዳዩን ላስፈፅሙ*።

አበል ስ ድርሻ፡ ክፍያ (በአይነት ወይም በገንዘብ የሚሰጥ)።

አባላ ግ እርስ በርስ አጣላ፡አናቆረ፡ አጋጨ።

አባላሽኝ ስ የፅኑ ረሃብ ወቅት ወይም ጊዜ።

ማባያ(መበያ) ስ ከእንጀራ፡ ከዳቦ፡...ጋር የሚበላ፡ ወጥ፡ በርበሬ፡...።

አብላላ ግ አሰላሰለ፡ አውጠነጠነ፡ አበሰለ (ሃሳብን)።

አስበላ ግ አሳጣ፡ አጋለጠ፡ ለክፉ ነገር (ለጠላት) አሳልፎ ሰጠ።

በላች "**በለተ**" ስር ተመ.

-በል "**በላ**" ስር ተመ.

በልቃጣ "**በለቀጠ**" ስር ተመ.

በልግ "**በለገ**" ስር ተመ.

በልጣጣ "**በለጠጠ**" ስር ተመ.

በሉጃ ስ ከወደ ቂጡ ድቡልቡልነት ያለው አጭር ዱላ፡ ከንተሮ።

በረሃ ስ 1.አየሩ በጣም ሞቃታማ፡ አፈሩ አሸዋማ፡ የሚያገኘው የዝናም መጠን እጅግ ዝቅተኛ የሆነ አካባቢ። 2. ጫካ፡ ውድማ፡ ሰው ያልሰፈረበት ቦታ ወይም አካባቢ።

በረሃ ገባ 1. ሸፈተ። 2. መነነ።

በረሀኛ ቅ በበረሃ የሚኖር።

በረሃማ ቅ የአየር ንብረቱ እንደ በረሃ ያለ ቦታ ወይም አካባቢ።

በረረ ግ 1. በአየር ላይ በክንፍ ሄደ፡ ከነፈ (አሞራ፡ ወፍ፡...)። 2.ሮጠ። 3. በአውሮፕላን

ሄደ፣ ተጓዘ።

በረራ ስ ጉዞ (የአውሮፕላን)።

በረር ስ በጎችን የኩልኩሌት በሽታ የሚያሲዝ ትል ወይም ጀርም።

በረሮ ስ ቀለሙ እንደ ትኋን የቀይ ቡኒ የሆነ መጠኑ ከጥንዚዛ አነስ ብሎ ጠፍጠፍ ያለ፣ ብዙውን ጊዜ ሙቀት ያለባቸውን ጨጋግማ አካባቢዎች (የማቀዝቀዣ ሞተር ፣ቴፕ፣ ሬድዮ፣ቴሌቭዥን፣ሳጥን፣ልብስ፣...)የሚያዘወትር ሲሄድ ፍጥነት ያለው የቤት ውስጥ ነፍሳት።

በረሮ

በራሪ ቅ 1. ክንፍ ያለው፣ በክንፍ የሚሄድ (ትንኝ፣ ዝንብ፣...)። 2. ፈጭ። 3. እንደ መደበኛዎቹ (ተረኞቹ) ተራ ወይም የመነሻ ሰአት ሳይጠብቅ ያገኘውን ሰው ብቻ ጭኖ ከተረኞቹ እየቀደመ የሚሄድ የህዝብ ማመላለሻ መኪና። 4. አውሮፕላን ላይ የሚሰራ የአስተ ተረኛ ተቀጣር። 5. ከአንድ በላይ ቅጂ(ኮፒ) እንዲኖራቸው ሲባል ተመሳሳይ የገፅ ቁጥር ከሚሰጣቸው የካርኒ ወረቀቶች ውስጥ የመጀመሪያው ቅጠል ወይም ወረቀት።

ብራሪ ቅ 1. ፍንጣሪ። 2. መጤ፣ ባይተዋር፣ አድራሻው ወይም የመጣበት ከየት እንደሆነ በውል የማይታወቅ (ሰው)።

ብራሮ ስ ሲቀላ ከምጣድ ላይ እየተፈናጠረ የሚወድቅ የእህል ቅንጣት።

ብር ብር አለ ግ በችኮላ፣ በፍጥነት ተንቀሳቀሰ፣ ተዘዋወረ፣ ወዲያ ወዲህ ሄደ። 2. ተርገበገበ፣ በፍጥነት ተንቀሳቀሰ(አይን፣ ልብ)።

ተባረረ ግ 1.(በስራ ምክንያት) በጥድፊያ ወዲያ ወዲህ አለ፣ ተዋከበ። *እረፍት የለውም ተባሮ ነው የሚኖረው*። 2. ተወገደ፣ ተገለለ። 3. ተሰደደ።

ተባራሪ ቅ 1. በሽሽት ላይ ያለ (ሰው)። 2. ቋሚ መኖሪያውን ትቶ ወደሌላ አካባቢ እንዲሰደድ የተደረገ።

ተባራሪ ወሬ ስ እርግጠኛነቱ የማይታወቅ፣ ተዛማች ወሬ።

ተባራሪ ጥይት ስ ኢላማውን ስቶ ወደ ሌላ አቅጣጫ የሄደ ጥይት።

አበረረ ግ 1. አሮጠ፣ አሳደደ። 2. አስወገደ። 3. ከስራ አሰናበተ። 4. በሃይል፣ በፍጥነት ነዳ፣ አሽከረከረ።

አብራሪ ቅ አውሮፕላን ነጂ።

አባረረ ግ 1.አሮጠ። 2. አሳደደ። 3. አስወገደ። 4. ተከታተለ።

መስተባርር ስ የተደገመበትን ሰው ከሚኖርበት ቤት፣ ቦታ የማባረር ሃይል አለው ተብሎ የሚነገርለት አስማት ወይም ድግምት።

አባራሪ ቅ 1.አሳዳጅ። 2. አንድን ነገር ስራዬ ብሎ የሚከታተል።

በረሰ ግ 1.ተሻረ፣ ረከሰ (መድሃኒት፣አስማት)። 2. ተበረዘ፣ በረደ፣ ቀዘቀዘ።

ማብረሻ ስ የመድሃኒት መሻሪያ፣ ማርከሻ።

በረቀ ግ ቦግ፣ ብልጭ፣ ፍልቅ አለ፣ ተብለጨለጨ።

መብረቅ(ብራቅ) ስ 1.የሰማይ ብልጭታን ተከትሎ የሚሰማ ከፍተኛ የፍንዳታ ድምፅ፣ ነጎድጓድ 2. ከፍተኛ ሙቀትና ሃይል ያለው፣ እጅግ በጣም ከፍተኛ በሆነ ፍጥነት ተምዘግዝጎና በሰውም ሆነ በንብረት ላይ አንዳንድ ጊዜ ጉዳት አድርሶ በቅፅበት ከእይታ ውጪ መሆን የሚችል የሰማይ ብልጭታ።

በረቅ ስ 1.መብረቅ። 2. ነጭ የሆነ የማእድን አይነት (አፈር፣ ድንጋይ)።

ብርቅርቅ ቅ ብልጭልጭ።

ብርቅርቅታ ስ ብልጭልጭታ።

ብርቅርቅ አለ ግ አብረቀረቀ።

ተብረቀረቀ ግ ተብለጨለጨ፣ ተፍለቀለቀ።

አበረቀ ግ ብልጭ አለ ወይም ብልጭ አደረገ (ሰማይ)።

አብረቀረቀ ግ አብለጨለጨ፣ አፍለቀለቀ፣ አንተገተገ (ብሃ፣ መስታወት፣...)።

በረቀሰ ግ 1. ነደለ፣ በሳ፣ በረገደ፣ ከፈተ። 2. አፈረሰ፣ ጣሰ፣ በጣጠሰ።

ተበረቀሰ ግ 1.ተነደለ፣ ተበሳ፣ ተበረገደ፣ ተከፈተ። 2. ፈረሰ፣ ተበጣጠሰ።

በረቅ "በረቀ" ስር ተመ.

በረቈ ግ 1. ነጣ፣ ገረጣ። 2. በሰለ፣ ደረሰ፣ ጎመራ(ሰብል)።

በረበረ ግ 1. ጎረጎረ፣ መረመረ፣ ፈተሸ፣ ፈለገ። 2.በዘበዘ፣ ዘረፈ፣ ሰረቀ። 3. በመወቃት ላይ ያለን ሰብል (ገብስ፣ ስንዴ፣...) የላዩን ወደታች፣ የታቹን ወደላይ አደረገ። 4. ሆድ እቃን አተረማመሰ፣ አገለባበጠ፣ ጤና ነሳ።*በበዶ ሆዴ*

አረቄ ጠጥቼ ሆዴን በረበረኝ።

በርባሬ ቅ 1.ዘራፊ፣ ቀማኛ፣ ከሰው ቤት ገብቶ የሰው ንብረት ዘርፎ የሚሄድ። 2. በመወቃት ላይ ያለን (እንደ ገብስ፣ ባቄላ፣...ያለን) ሰብል የላዩን ወደታች፣ የታቹን ወደላይ ለማድረግ በመንሽ የሚገለብጥ (ሰው)።

ብርባሮ ስ በመወቃት ላይ ያለን እህል ወይም ሰብል በመንሽ የመገልበጥ ስራ።

እንቡርባይ ስ በመንሽ ተበርብሮ የወጣ ያልደቀቀ ገለባ፣ እንግውላይ።

በረታ ግ 1.ጠነከረ፣ ጎለበተ፣ ሃይል አገኘ። 2. አየለ፣ ተጋነነ፣ ጎላ (ነገር፣ ጥል)። 3. አገገመ፣ ተሻለው።4.ተፍጨረጨረ፣ጎበዘ፣ታገለ። *በትምህርቱ በርትቷል*። 5.ተበረታታ፣ ተፅናና (ለሃዘን)።

ብርቱ ቅ ፅኑ፣ ጠንካራ፣ ጎበዝ።

ብርቱ ነዎት? ጤንነትን፣ ደህንነትን በተመለከተ የሚቀርብ የሰላምታ ቃል።

ብርቱ ጉዳይ ስ በጣም አስፈላጊና ጥብቅ የሆነ ነገር፣ ስራ።

ብርታት ስ ሃይል፣ ፅናት፣ ጥንካሬ፣ ጉልበት።

ተበረታታ ግ ተጠናከረ፣ ተፅናና፣ ጎበዘ።

ተበራታ ግ ተበረታታ።

አበረታታ ግ 1.እንዲበረታ፣ እንዲጠነክር አገዘ፣ ገፋፋ፣ ደገፈ። 2.አፅናና።

ማበረታቻ ስ ማጠናከሪያ፣ ማፅናኛ (ስጦታ፣ ሽልማት፣...)።

በረት ስ እንደ ከብቶች፣ በጎች፣... ያሉ እንስሳት የሚያድሩበት ቤት።

በረት ነው በጣም ሰፊ ነው (ለቤት)።

በረት አፍ(ስድብ) 1. አፉ ሰፊ የሆነ (ሰው)። 2. እንደፈለገ የሚናገር፣ መጥፎ ተናግሮ ሰውን የሚያስቀይም (ሰው)።

በረንዳ ስ በቤት ዋና በር፣ በስተውጪ በኩል ከቤቱ ጣሪያ ጋር ተያይዞ የሚሰራ፣ ብዙውን ጊዜ በአንድ በኩል ብቻ ግድግዳ የሚኖረው የቤቱ የውጪ አካል(ስእሉን ቤት ስር ተመ.)።

በረንዳ አዳሪ ቅ 1.የሚያድርበት ወይም የሚጠለልበት ቤት የሌለው፣ ብዙውን ጊዜ በከተማ ውስጥ በየመንገዱ ዳር በሚገኙ ታላላቅ ህንፃዎች ታዛ ስር ወይም በየጥጋ ጥጉ ተኝቶ ሌሊቱን የሚያሳልፍ ሰው፣ ቦዘኔ። 2. (ዘይ.፣ስድብ) ወሮበላ፣ ዱርዬ አዳሪ፣ ወስላታ፣ ሌባ፣ ቀማኛ። ቅ 3. ዘዋሪ፣ በቋሚነት ስራ ላይ በመዋል ፈንታ በስራ ፈትነት ሲያውደለድል የሚውል።

በረኛ "በር" ስር ተመ.

በረከ ግ ጉልበቱ ራደ፣ ተንቀጠቀጠ፣ አቅም አጣ።

ብርክ ስ ከድንጋጤና ከፍርሃት የተነሳ በድንገት አቅመቢስ መሆን፣ መድከም፣ መዛል፣ መርበትበት፣ መልፈስፈስ።

ብርክ ያዘው በድንገተኛ ድንጋጤ ምክንያት ጉልበቱ ተልፈሰፈሰ፣ መንቀሳቀስ ተሳነው።

ብርክርክ ቅ ቀጥቃጣ፣ ድንጉጥ፣ ፈሪ።

ብርክርክ አለ ግ ተብረከረከ።

ተብረከረከ ግ 1.አቅም አጣ፣ ጉልበቱ ራደ፣ ተንቀጠቀጠ። 2.ፈራ፣ ተርበደበደ፣ ተርበተበተ።

አብረከረከ ግ 1. አርገደገደ፣ አልፈሰፈሰ፣ አቅም አሳጣ። 2. አስፈራ፣ አርበደበደ፣ አራደ፣ አንቀጠቀጠ፣ አርበተበተ።

በረከተ ግ 1. በዛ፣ መጠኑ ጨመረ። 2. ተረፈ፣ ተትረፈረፈ። 3. ብዙ ቆየ፣ ሰነበተ(ለአላቂ ነገሮች)።

በረከት ስ 1. ረድኤት፣ መቅኖ። 2. ስጦታ። *እነሆ በረከት*። 3. ፀጋ፣ ምርቃት።

በረከት የለውም ረድኤት፣ መቅኖ የለውም።

በረከት ያውርድ ይባርክ፣ ይትረፍረፍ፣ ይበርክት፣ ረድኤት ያግኝ ለማለት የሚባል የበጎ ምኞት መግለጫ ወይም ምርቃት የሚነገርበት ቃል።

በረከተ ስጋ ስ ስጋዊ ፀጋ፣ ሃብት፣ ምድራዊ ብልፅግና።

በረከተ ቢስ ቅ ረድኤት የሌለው፣ አሲጻም።

በርካታ ቅ አያሌ፣ ብዙ።

ብርኩቴ ስ 1.ብዛት። 2. ረድኤት፣ መቅኖ።

ተበረከተ ግ ተሰጠ (ስጦታ)።

ተበራከተ ግ እየበዛ ሄደ፣ ተትረፈረፈ።

አበረከተ ግ ሰጠ (ገፀበረከትን)።

***በረከከ**

በርከክ አለ ግ ተንበረከከ።

ተንበረከከ ግ 1. በጉልበቶቹ ቆመ፣ መሬት ነካ። 2.(ዘይ.) ተሸነፈ፣ ታዛዥ፣ ተገዥ ሆነ።

አንበረከከ ግ 1. በጉልበት አስቆመ። 2. አሸነፈ፣ የበታች አደረገ፣ ገዛ፣ አስገበረ።

እንብርክክ (እንብርክ) ስ በጉልበት መሬት የመንካት ወይም መሬት ላይ የመቆም ድርጊት።

በእንብርክክ (በእንብርክ) ያስኬዳል ሃይለኛ ነው፣ ያሰክራል። *ጠላው በእንብርክክ ያስኬዳል።*

በረኪና ስ ያደፈን ወይም የመነቸከን ነጭ ልብስ ለማፅዳት እንዲያግዝ ከውሃና ከሳሙና ጋር እየተደባለቀ ልብስ የሚታጠብበት ፈሳሽ የሆነ

ኬሚካል።

በረካ ስ በሃገር ባህል መሰረት ቡና በጀበና በሚፈላበት ጊዜ ከአቦሉና ከሁለተኛው ቀጥሎ የሚጠጣው ቡና ፤ ሶስተኛ ቡና።

በረካ ሁን (ምር.) የተባረክ፥ የተቀደስክ ሁን።

በረኮተ ግ ሊጥን በጋለ ድንጋይ ወይም በፍም ላይ አስቀምጦ ርሚጦ ወይም ቂጣ ጋገረ፥ አበሰለ።

ብርኩታ ስ ርሚጦ፥ በጋለ ድንጋይ ወይም በፍም ላይ ተደርጎ የበሰለ ቂጣ።

በረዘ ግ 1.ማርን በውሃ በጥብጦ ብርዝ አዘጋጀ። 2. የጠላን ድፍድፍ በውሃ በጠበጠ፥ አቀጠነ፥ ሞላ። 3. ሃይለኛውን መጠጥ ለስላሳ ካለው ጋር ደባለቀ፥ ቀየጠ። 4. ሙቅ ውሃን ከቀዝቃዛ ጋር ደባለቀ፤ ከለሰ።

ብርዝ ስ ጌሾ የማይገባበትና ማርን በውሃ በቀጭኑ በመበጥበጥ የሚዘጋጅ የመጠጥ አይነት።

ተበረዘ ግ ተመረዘ፥ ተበላሸ። *አእምሮው በመጥፎ አስተሳሰብ ተበረዘ።*

ተባረዘ ግ አንዱ ከሌላው ጋር ተቀላቀለ፥ ተቀየጠ፥ ተደበላለቀ (ለፈሳሽ)።

አበረዘ ግ አበረደ፥ አበረሰ፥ አቀዘቀዘ።

አባረዘ ግ አቀላቀለ፥ አደባለቀ፥ ከለሰ።

በረየ ግ በረገገ፥ ደነበረ፥ ሸሸ። *እባብ ያየ በልጥ በረየ።*

***በረየ**

ተበራየ ግ ከማሳ የተሰበሰበው ሰብል ውድማ ላይ ተደርጎ በከብት እግር እንዲረገጥ ሆነ (ፍሬውን ከገለባው ለመለየት)።

አበራየ ግ ከእርሻ ቦታ የተሰበሰበን ሰብል ውድማ ላይ አድርጎ በከብት እግር አስረገጠ፥ ወቃ፥ አሄደ።

በረደ ግ 1. ቀዘቀዘ፥ ሙቀት አልባ ሆነ። 2 . ቆፈነነ፥ ብርድ ሆነ። 3. ተረጋጋ፥ ሰላም ሆነ። *ጠቡ በረደ።* 4. ከዝሙት ስራ ራቀ፥ ጨመተ።5.ደነዘ፥ አልቆርጥ፥ አልፈልጥ አለ። *ስለቱ በረደ።*

በረድ የ"**በረዶ**"ን አንደኛ ፍቺ ተመ.

በረዶ ስ 1. እጅግ በጣም ከመቀዝቀዙ የተነሳ ወደ ጠጣርነት የተለወጠ ውሃ፤ በረድ። 2. በጣም ቀዝቃዛ። *እጁ በረዶ ነው።*

በረዶ ቤት ስ ምግብና መጠጥ ለማቀዝቀዝ ወይም ሳይበላሽ ረዘም ላለ ጊዜ እንዲቆይ ለማድረግ የሚረዳ በረዶ ያለበት ቤት፥ ክፍል፥ እቃ።

በረዳማ ቅ በረዶ በብዛት ያለበት (ቦታ)።

በራዳ (በራድ) ቅ በጣም ቀዝቃዛ።

ብርድ ስ 1. ቁር፥ ቆፈን፥ ውርጭ፥ በጣም የሚቀዘቅዝ አየር። 2. በቀዝቃዛ አየር ምክንያት የሚያጋጥም ህመም።

ብርድ መታው 1. የብርድ በሽታ ያዘው። 2. በቀዝቃዛ አየር ምክንያት ብልሽት አገኘው (ሰብል)።

ብርድ ብርድ አለው ከብርድ ጋር የተያያዘ ወይም ከብርድ ጋር የተመሳሰለ የህመም ስሜት ተሰማው።

ብርድ ፈደፈደው ቀዝቃዛ አየር ሰውነቱን አሰቃየው።

ብርድ ልብስ ስ ከጥጥ ወይም ከሱፍ፥... የሚሰራና በመኝታ ጊዜ ሰዎች ለሙቀት የሚለብሱት እንደ ማቅ፥ ዝተት፥ ባና ያለ ወፍራም ልብስ።

ብርዳም (ብርዳማ) ቅ ሃይለኛ ቅዝቃዜ ያለበት(ቦታ፥ ወቅት)።

ተባረደ ግ 1. አየሩ ቀዘቀዘ፤ የቅዝቃዜ ስሜት አሰማ፥ ፈጠረ። 2. ተባረዘ፥ ተከለሰ (ሙቅና ቀዝቃዛ ውሃ)።

አበረደ ግ 1. አቀዘቀዘ፥ ሙቀቱ እንዲቀንስ አደረገ። 2. አስታገሰ፥ አስወገደ። *በመካከላቸው ገብቶ ጥሉን አበረደ።*

ማብረጃ ስ የሹርቤ፥ ብርሌ ቅርፅ ያለውና ከብርሌ ላቅ ያለ የጠላና የጠጅ መያዣ ጠርሙስ።

አብራጃ ቅ ቀዝቃዛ፥ ነፋሻ (ቦታ)።

በረደደ ግ ጠና፥ በረታ፥ ጠነከረ።

በረድድ(ብርድድ) ቅ ፅኑ፥ ብርቱ፥ ጠንካራ።

በረድ "በረደ" ስር ተመ.

በረዶ ዝ.ከ.

***በረጀረጀ**

ተብረጀረጀ(ተብረገረገ) ግ 1.በመጠጥ ወይም በሌላ ምክንያት ሰውነቱ ዛለ፥ ፈዘዘ፥ ተርገፈገፈ፥ ተንቦገቦገ። 2. ተጥበረበረ (አይን በነፀብራቅ)።

አብረጀረጀ(አብረገረገ) ግ 1.ሰውነትን አዛለ፥ አደከመ፥ አርገፈገፈ፥ አንቦገቦገ። 2. አይንን አጥበረበረ (ነፀብራቅ)።

በረገደ ግ 1. ሙሉ በሙሉ ከፈተ፥ ወለል አደረገ (ብዙውን ጊዜ ሃይልና ፍጥነት በተቀላቀለበት ሁኔታ)። 2. ከሁለት ከፈለ፥ ሰነጠቀ። *ግንዱን በመጥረቢያ በረገደው።*

በርጋዳ(ብርግድ) ቅ 1.ያልተዘጋ፥ የማይዘጋ፥ ክፍት። 2. (ስድብ) ስትቀመጥ፥ስትሄድ መሸፈን ያለበትን የሰውነቷን ክፍል የማትሸፍን፥ እርቃኗን

ስለ መጋሰሱ የማትጨነቅ፥ የማትጠነቀቅ።

ተበረገደ ግ 1. ተከፈተ፥ ወለል አለ። 2.ተከፈተ፣ ተሰነጠቀ።

ተበራገደ ግ በአቋቋም፥ በአነሃሄድ፥ በአቀማመጥ እግሮቹን በጣም ከፈተ።

በረገገ ግ ደንግጦ ሸሸ፥ በረየ፥ደነበረ።

በርጋጋ ቅ ድንጉጥ፣ ፈሪ፣ ደንባሪ።

ብርግግ ብርግግ አለ ከፍርሃት፣ ከድንጋጤ የተነሳ ብትት ብትት አለ፣ ሰውነቱ የድንጋጤ እንቅስቃሴ አደረገ።

ተበራገገ ግ ተደናገጠ፥ ተደናበረ።

***በረጠጠ**

በርጣጣ ቅ ኩራተኛ፣ ጉረኛ፣ ትእቢተኛ፥ በጥራራ።

ተንበራጠጠ ግ ኮራ፥ ታበየ፣ ተንበጣረረ።

አንበራጠጠ ግ አኮራ፥ አንበጣረረ።

በራ (ራስ በራ) ቅ ፀጉሩ ከሠደ ግንባሩ የሸሸ፥ የተመለጠ (ሰው)።

በራ^1 ግ 1. ቦግ አለ፤ ብርሃን ሆነ። 2. ነጣ ፥ ፈካ፣ ብሩህ ሆኖ ታየ።

መብራት ስ ከችቦ ወይም ከሻማ ወይም ከጧፍ እሳት፥...የሚገኝ ወይም ከኤሌክትሪክ ሃይል የሚመነጭ ብርሃን።

መብራት ሃይል ስ 1. የኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫውንና የአስተዳደሩን ጉዳይ አጠቃሎ የሚመራ መስሪያ ቤት። 2. የኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ጣቢያ።

ብሩህ (ብሩ) ቅ የበራ፣ የፈካ፣ ንፁህ፣ የጠራ።

ብሩህ አእምሮ ስ ነገሮችን በፍጥነት መረዳት የሚችል አስተዋይ አእምሮ።

ብርሃን ስ 1. የመብራት፣ የፀሃይ፥...ወጋጋን፣ የጨለማ ተቃራኒ። 2. ፋና፥ መብራት። 3. ቀን፣ ፀሃይ ወጥታ እስክምትጠልቅ ያለው ጊዜ።4. የአይን የማየት ችሎታ። *ብርሃኑን ያጣው አንዲል ላይን ሰውር።*

ብርሃነ ልደት ስ ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደበት እለት፣ በአለ ልደት፣ ልደት።

ብርሃነ ትንሳኤ ስ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ከመቃብር የተነሳበት እለት፣ በአለ ትንሳኤ፣ ትንሳኤ።

ብርሃነ ጥምቀት ስ ኢየሱስ ክርስቶስ በዮርዳኖስ ወንዝ በዮሃንስ እጅ የተጠመቀበት እለት፣ በአለ ጥምቀት፣ ጥምቀት።

ተብራራ ግ ተፍታታ፥ ግልፅ እንዲሆን ተደረገ (ሃሳብ)።

አበራ ግ 1. መብራት ለኮሰ፥ ብርሃን እንዲሆን አደረገ። 2. ቦግ አለ፥ አብለጨለጨ፤ አንፀባረቀ። 3. አዳነ፥ ፈወሰ (የታወረ አይንን)።

ማብሪያ ማጥፊያ ስ የኤሌክትሪክ አምፖል ወይም ሌላ በኤሌክትሪክ ሃይል የሚሰራ መሳሪያ እንዲበራ ወይም እንዲጠፋ ለማድረግ የሚያገለግል የኤሌክትሪክ እቃ።

አብራራ ግ ተነተነ፥ ግልፅ አደረገ፥ በሚገባ አስረዳ (ሃሳብን) ።

ማብራሪያ ስ ግልፅነት የጎደለውን ሃሳብ ግልፅ ለማድረግ የሚረዳ መግለጫ።

በራ^2 ግ ዝናም መዝነሙን አቆመ፥ ብራ ሆነ።

ብራ ስ ዝናም የቆመበት ወይም የሌለበት ጊዜ።

ብራ ሆነ ዝናም ቆመ፥ ጠፋ።

አበራ ግ ዝናም መጣሉን ተወ፥ አቆመ።

በረራ **"በረረ"** ስር ተመ.

በራድ^1 ስ የሻይ ማፍሊያ ወይም ማቅረቢያ ማንቆርቆሪያ።

በራድ^2 **"በረደ"** ስር **"በራዳ"**ን ተመ.

በራፍ **"በር"** ስር ተመ.

በሬ ስ ከቀንድ ከብት ወገን የሆነ፥ ብዙውን ጊዜ ለእርሻ ስራ የሚያገለግል ተባእት የቤት እንስሳ(ስእሉን የቤት እንስሳ ስር ተመ.)። 2. (ዘይ.፥ ስድብ) ሞኝ፥ ቂል።

በሬ ወለደ የሚል ቅንጣት ያህል እንኳ እውነትነት የሌለው ወሬ የሚያወራ።

የበሬ ልብ ስ መጠኑ ብርቱካን የሚያህል፥ ቅርፁ ልብ የሚመስል የፍራፍሬ አይነት።

የበሬ ሽንት ስ ቀጥታነት የሌለው፣ አንድ ጊዜ ወደቀኝ አንድ ጊዜ ወደግራ እየተጠማዘዘ የሚሄድ የመስመር ቅርፅ፥ መንገድ።



የበሬ ሽንት

የበሬ ግንባር የምታህል በጣም ትንሽ የሆነች (መሬት)።

በር ስ 1. ሰውም ሆነ ሌላ ነገር ሊተላለፍበት እንዲችል የተወሰነ ክፍተት እንዲኖረው ተደርጎ የተሰራ፥ ሲያስፈልግ ክፍተቱ በመዝጊያ ሊከለል የሚችል የቤት ወይም የግቢ መግቢያና መውጫ፤ መተላለፊያ (ስእሉን ቤት ስር ተመ.)። 2.

መዝጊያ። 3. ኳስ፡ ከአንድ የተወሰነ የቦታ ክልል ወደሌላው ለመሄድ እንደ መተላለፊያ የሚያገለግል መንገድ።

በር መታ በር አንኳኳ፥ ደበደበ፡ ቆረቆረ።

በር አወጣ ለመተላለፊያ ወይም ለመግቢያና ለመውጫ እንዲያገለግል በር አበጀ፡ ሰራ።

ከበር መልስ ከቤት በር ጀምሮ ወደ ውስጥ ያለው ሁሉ በጠቅላላ።

በራፍ(በር አፍ) ስ ወደቤት ወይም ወደግቢ ለመግባትና ከቤት ወይም ከግቢ ለመውጣት እንደመተላለፊያ የሚያገለግል የቤት ወይም የአጥር በር፡ ደጃፍ።

በር ጠባቂ ስ ዘበኛ፥ ዋርዲያ፥ በረኛ።

በረኛ ስ 1. በር ጠባቂ፡ ዘበኛ። 2. በእግር ወይም በእጅ ኳስ ጨዋታ ጊዜ ኳሷ ወደ ግብ እንዳትገባ የሚከላከል፡ የሚጠብቅ ተጫዋች፥ ግብ ጠባቂ።

በርሜል(በርሚል) ስ ከእንጨት ወይም ከቆርቆሮ ወይም ከፕላስቲክ የሚሰራና ለጠጅ መጣያ ወይም ለጠላ መጥመቂያ ወይም ለሌላ ነገር መያዣ የሚያገለግል ትልቅ እቃ።

በርሞሌ ስ የሽቶ ስም።

በርበሬ ስ 1. የበሰለ፡ የጎመራ ወይም ከመብሰሉ የተነሳ ወደ ቀይነት የተለወጠ የቃሪያ ተክል ዛላ። 2. ከበሰለ ወይም ከጎመራ የቃሪያ ዛላ በድልህ ወይም በአዋዜ ወይም በዱቄት መልክ የሚዘጋጅ ሲበሉት የሚፋጅ ወይም የሚያቃጥል የወጥ ቅመም። 3. ከላይ የተገለፀውን ዛላ የሚያፈራ ተክል።

በርባሬ "በረበረ" ስር ተመ.

በርባሮስ ስ መቀመቅ፡ ሰፊና ጥልቅ የሆነ ጉድጓድ።

በርኖሴ ስ ፀረ እህል ተባይ፡ ተምች።

በርኖስ ስ ከጥቁር የበግ ፀጉር የሚሰራ፥ እንደ ካባ ከኩታ በላይ ተደርቦ የሚለበስ ወፍራም ልብስ(ስእሉን ልብስ ስር ተመ.)።

በርካታ "በረከተ" ስር ተመ.

በርዳዳ "በረደደ" ስር ተመ.

በርጋዳ "በረገደ" ስር ተመ.

በርጋጋ "በረገገ" ስር ተመ.

በርጣጣ "*በረጠጠ" ስር ተመ.

በርጩማ ስ 1. ቅርፁ ክብ ሆኖ መሃሉ ጎድጎድ ያለ፥ ከአንድ ግንድ ውጥ ሆኖ የተሰራ ባለ ሶስት እግር መቀመጫ፡ ወንበር። 2. ሁለት አጫጭር እግሮች ያሉት የእንጨት መቀመጫ፥ አነስተኛ አግዳሚ ወንበር።



በርጩማ 1ኛ ፍቺ

በሰለ ግ 1. ለምግብነት ደረሰ፡ ጎመራ (ሰብል፡ ፍራፍሬ)። 2. አንድ የምግብ አይነት(ጥሬ ሥጋ፥ ሊጥ፥...) በመቀቀል ወይም በመጋገር፥... ለምግብነት ከሚያበቃው ደረጃ ላይ ደረሰ 3. ዳበረ፥ በሰፀ (አእምሮው በእውቀት)። 4. ቆሰለ፥ ተጎዳ፥ በጣም ተናደደ(አእምሮው በነገር)። 5. ለፍፃሜ ደረሰ፡ ተቃረበ(ጉዳይ)። 6.ህመሙ ለመዳን ተቃረበ፡ ሲቃዥ ቀነሰ (ለምሳሌ ጉንፋን)። 7. መግል ያዘ፡ ሊፈነዳ ደረሰ (ያበጠ ቁስል)። 8.ብዙ ከመቆየቱ የተነሳ በነ፥ ከመጠጠ (ቅቤ)። 9.ሳይመስልበት ጠነከረ፡ ጠጠረ፡ ጉልበት አወጣ(ልጅ)። 10. ነፍስ አወቀ፡ ክፉና ደግ ለየ (ልጅ)።

የበሰለ ቅቤ ስ የቆየ፡ የበካ ቅቤ።

በሰላ ስ 1. ታርሶ ለዝሪት የተዘጋጀ፡ የለሰለሰ እርሻ ወይም ማሳ። 2. ለባለእዳ መክፈል ያለበት ገንዘብ።

የበሰላ ዋስ ስ እዳን የመክፈል ሃላፊነት ያለበት ዋስ።

በሰሎ ስ ተዘጋጅቶ የተቀመጠ ምግብ፡ መሰነጥ።

በሳል ቅ 1.ሲቀቅሉት ቶሎ የሚበስል (ጥራጥሬ ወይም ተክል)። 2. ብዙ የቆየ፡ የጠነከረ። 3. በትምህርት፥ በእውቀት፥...የበሰፀ።

ብሳይ ቅ በጉድጓድ ተጠራቅሞና ተብላልቶ የቆየ (አዛባ፡ ፍግ)።

ብስል ቅ 1.የጎመራ፡ ለምግብነት የደረሰ (ፍራፍሬ)። 2. ተቀቅሎ ወይም ተቆልቶ፡... የሚገኝ (ምግብ)። 3. (ዘይ.)ሁ• አዋቂ፥ ማመዛዘን የሚችል (ሰው)። ሰ• ብልህ፥ ብልጥ።

ብስል ቀይ በጣም ቀይ የሆነ።

ብስል ተቀሊል ከጥሬው ወይም ከመጥፎው ብቻ ያልሆነ፡ ሁለቱም ተቀላቅለው የሚገኙበት።

ብስለት ስ 1. የመጎምራት፡ ለምግብነት የመድረስ ሁኔታ (ለፍራፍሬ)። 2. (ዘይ.) ሁ• እውቀት፥ አዋቂነት። ሰ•ብልህነት፡ ብልጠት።

ተባሰለ ግ በነገር ተቋሰለ፡ ተበሻሸቀ፥ በጣም ተቃቃረ።

አበሰለ ግ 1. ምግብ አዘጋጀ (በመቀቀል፡ በመጋገር፡...) 2. በጣም አመመ፡ ጎዳ (በሽታ)።

3. በሃይል፡ በጣም አጥብቆ አደረገ፤ ከመነ። *ሳብሶ ተማረ።*

ማብሰያ ስ 1. የምግብ ማዘጋጃ (መቀቀያ፥ መጋገሪያ፥...)እቃ። 2. ለምግብ ማዘጋጃ የሚያገለግል ማገዶ።

አብሳይ ስ ምግብ አዘጋጅ (በመቀቀል፡ በመጋገር፥...)።

አብስል ቅ አናዳጅ፡ አብሻቂ።

***በሰረ**

ብስራት ስ የምስራች፡ መልካም ዜና።

ተበሰረ ግ የምስራቹ ወይም ብስራቱ ተነገረ፡ ተወራ።

አበሰረ ግ የምስራች አለ፡ መልካም ወሬ ወይም ዜና ተናገረ።

አብሳሪ ቅ ብስራት ወይም የምስራች ነጋሪ።

በሰቆለ ግ ተንገላታ፡ ተጉላላ፤ ጎስቆለ።

በስቋላ(ብስቁል) ቅ ችግር ያንገላታው፡ የተጉላላ፤ ጎስቋላ።

ብስቁልና ስ እንግልት፡ መጉላላት፡ ጉስቁልና።

ተበሳቆለ ግ ተንገላታ፡ ተጉላላ፥ ተጎሳቆለ።

በሰበሰ ግ 1. በውሃ ወይም ፈሳሽ በሆነ በሌላ ነገር ራሰ፡ ረሰረሰ፤ ረጠበ። 2. ንፅህናው ባለመጠበቁ ወይም አየር ሳያገኝ ታፍኖ በመቀመጡ ወይም በሌላ ምክንያት ተበላሸ፤ መጥፎ ጠረን ወይም ጣእም ፈጠረ። 3. በጣም አደፈ፡ ቆሸሸ (ለምሳሌ ልብስ)። 4. ክብክቤ ባለማግኘቱ ወይም እድሜውን በመጨረሱ ከጥቅም ውጪ ሆነ፡ ነገሰ። *የግድግዳው እንጨት ስለ በሰበሰ ቤቱ ተገረሰሰ*። 5. ፈረሰ፡ ፈራረሰ፡ ወደ አፈርነት ተለወጠ። 6. (የን.አነ.) በጣም አረጀ፡ ሸመገለ። 7. በአንድ በተወሰነ ቦታ ላይ በመሆን ብዙ ጊዜ አሳለፈ፡ እዚያው አረጀ፥ ተረሳ። *በወጣትነቱ እንደታሰረ ወህኒ ቤት በሰበሰ ቀረ*።

ብስባሽ ቅ የበሰበሰ፡ ቆሻሻ፡ ውድቅዳቂ።

ብስብስ(በሰበስ፥በስባሳ) ቅ 1. የቆሸሸ፡ የተበላሸ፡ የበሸቀጠ። 2. (ስድብ) ሁ(ነውር) ግም፡ ክርፋታም። ሰ. ያረጀ።

ተበሰበሰ ግ በመጠነኛ ውሃ እየታሸ እንዲርበ ተደረገ (ለበሶ ዱቄት)።

ተበሳበሰ ግ ተበሸቀጠ፥ ተግማማ፥ ተበላሸ።

አበሰበሰ ግ በሶን ወይም ለእንኩሮ የተዘጋጀን ዱቄት ከመጠነኛ ውሃ ጋር እያቦካ አሸ፥ አዘጋጀ።

አበሳበሰ ግ አበሸቀጠ፡ አግማማ።

በሰኛ ግ የማይስማማ ምግብ በመመገቡ መጥፎ ጠረን ያለው ግሳት አገሳ።

ብስና ስ የማይስማማ ምግብ በመመገብ ወይም በሆድ መታወክ ምክንያት የሚፈጠር፥ መጥፎ ጠረን ያለው ከሆድ የሚወጣ ግሳት።

ብስናታም ቅ (ስድብ) ክርፋታም፥ ግማታም።

በሰከ ግ በትንሹ በሬት አደረገ፥ በጠቀ፥ በጨቀ፥ ቀደደ።

ብስክ ቅ ብጥቅ፡ ቡጭቅ።

ብስክ ብስክ አለ ግ ብጥስ ብጥስ አለ (ለምሳሌ. ክር)።

ብስክስክ ቅ 1.ብጥስጥስ፥ ብትክትክ። 2. (ዘይ.) ንጭንጭ፡ ብስጩ።

ተበሰከ ግ ተበጠሰ።

ተበሳሰከ ግ ተበጣጠሰ።

ተብሰከሰከ ግ 1. አቅም አጣ፡ ተበጣጠሰ። 2. (ዘይ.) ተነጫነጨ፥ ተበሳጨ።

አብሰከሰከ ግ አቅበጠበጠ፡ ብስጭትጭት አደረገ፡ አነጫነጨ።

***በሰጨ**

ብስጩ ቅ ቁጡ፡ ተናዳጅ፡ ተነጫናጭ።

ብስጭት ስ ንዴት፡ መነጫነጭ፡ የህሊና ሰላም ማጣት።

ብስጭት አለ ግ ተበሳጨ፡ ተናደደ፥ ተነጫነጨ።

ተበሳጨ ግ ተናደደ፡ ተነጫነጨ፡ ተቆጣ።

አበሳጨ ግ አናደደ።

በሳ ግ ሸነቆረ፡ ነደለ፡ ቀደደ።

መብሻ ስ መሸንቆሪያ፡ መንደያ (መብሪያ)።

ብስ ቅ ሽንቁር፥ ቀዳዳ።

ተበሳ ግ ተሸነቆረ፡ ተቀደደ።

በሳል "በሰለ" ስር ተመ.

በስቋላ "በሰቆለ" ስር ተመ.

በስባሳ "በሰበሰ" ስር **"ብስብስ"** ን ተመ.

በስተ ___ አቅጣጫን ከሚያመለክቱ ቃላት በፊት እየገባ በ ___ በኩል የሚለውን ፍቺ የሚያመጣ ምእላድ። *በስተሰሜን/ በስተቀኝ/ በስተዚያ*።

በስተሂላ 1. ከሂላ፡ ከጀርባ። 2. ቆይቶ በመጨረሻ ጊዜ። 3. ከሂላ በኩል።

በስተርጅና በእርጅና ጊዜ___።

በስቲያ ወዲያ። *ከነገ በስቲያ እመለሳለሁ*።

በሶ ስ ዱቄቱ በውሃ እየተራሰ ከታሸ በኋላ እየተጨበጠ የሚበላ፡ ተቆልቶ ከተፈጨ ገብስ

የሚዘጋጅ የምግብ አይነት።

በሶብላ ስ ጥሩ ሽታና ጣእም ያለው የወጥ ቅመም አይነት፣ ዘቃቅቤ።

በሸረከ ግ ሸረከተ፥ ቀደደ፥ በሸከተ።

በሽረክ(በሽራካ) ቅ ሽርክት፥ ቀዳዳ።

ተበሸረከ ግ ተሸረከተ፥ ተቀደደ።

በሸቀ^{1} ግ ተበሳጨ፥ ተናደደ።

አብሽቅ(አብሻቂ) ቅ አናዳጅ።

በሸቀ^{2} ግ ረጠበ፥ ራሰ፥ በሰበሰ።

ብሽቅ ቅ የበሰበሰ፥ የገማ።

በሸቀጠ ግ 1. አደፈ፥ ቆሸሸ። 2. ራሰ፥ በሰበሰ። 3. ገማ፥ ሸተተ።

በሸቀጥ(ብሽቅጥ፥ በሽቃጣ) ቅ (ለድብ) ገም፥ በስባሳ።

ተበሻቀጠ ግ ተግማማ፥ ተበሳበሰ።

አበሻቀጠ ግ አኪያኪያሰ፥ አራከሰ፥ አጥላላ፥ አቃለለ፥ አዋረደ።

***በሸበሸ**

በሽ(በሽ) ነው ሞልቷል፥ ተርፏል፥ የተፈለገውን ያህል ይገኛል። *ጠጁ በሽ በሽ ነው።*

ተንበሸበሸ ግ የፈለገውን ያህል አገኘ፥ ረካ።

አንበሸበሸ ግ የተፈለገውን ያህል በመስጠት ደስ አሰኘ፥ አረካ።

በሸተ ግ አመመ፥ አወከ (ሆድን)።

በሽታ ስ ህመም።

በሽታ ላይ ወደቀ ታመመ፥ በሽተኛ ሆነ።

በሽታ ሸመተ/ገበየ/ገዛ/አተረፈ/ አፈራ በሽታ ያዘው፥ አጋጠመው።

በሽተኛ ቅ በሽታ የያዘው፥ ያደረበት፥ ህመምተኛ።

ተበሸተ ግ ታመመ፥ ታወከ። *ሆዱ ተበሽቷል።*

በሽራካ "በሸረከ" ስር **"በሽረክ"**ን ተመ.

በሽቃጣ "በሸቀጠ" ስር **"በሸቀጥ"** ን ተመ.

በሽታ "በሸተ" ስር ተመ.

በሽ አለው "ብሽ" ስር **"ብሽ አለው"**ን ተመ.

በቀለ ግ 1.አጎነቆለ፥ የብቅል ጥሩ አወጣ (በውሃ ተርሶ የተቀመጠ እህል)። 2. ከማሳ ላይ የተዘራው ዘር (የእህል ወይም የሌላ እፅዋት ፍሬ) ተስማሚውን አፈር፥ አየርና ርጥበት ሲያገኝ እምቦቀቅላ ግንዱንና ቅጠሉን በትንሹ ከአፈር ውስጥ ብቅ አደረገ፥ ፀደቀ። 3. በዛ፥ አቆጠቆጠ (ፀጉር)።

__በቀል ቅ 1. ሆኖ የበቀለ፥ የወጣ፥ የተገኘ። *አንድ በቀል ዛፍ።* 2. __ኗሪ፥ አደግ። *ላብር በቀል።* 3. የ__ውስጥ። *አገር በቀል።*

በቆልት (በቀልት፥ በቆልቲ) ስ በውሃ ርሶ የበቀለ ወይም የጎነቆለ ባቄላ ወይም ሌላ ጥሬ።

ቡቃያ(ብቋያ) ስ አዲስ የበቀለ ወይም ከበቀለ ብዙ ጊዜ ያልሆነው፥ በማደግ ላይ ያለ የእህል ሰብል።

ብቅል ስ ጠላ ለማዘጋጀት (ለመጥመቅ) ከሚያስፈልጉት ነገሮች አንዱ የሆነ፥ ለተወሰነ ጊዜ በውሃ ርሶ ከቆየ በኋላ በቅጠል ተሸፍኖ ጉድጓድ ውስጥ ወይም በተመሳሳይ ቦታ እንዲቀመጥ ተደርጎ የበቀለ ገብስ ፥ ስንዴ፥...።

ብቅል ረገጠ ገብስን ወይም ስንዴን ለተወሰነ ጊዜ በውሃ ውስጥ ነክሮ ካቆየ በኋላ ከውሃው ለይቶና ጉድጓድ ውስጥ በቅጠል ጀቡኖ በማስቀመጥ ብቅል እንዲሆን አደረገ።

ብቅል አውራጅ በጣም ረዥም የሆን (ሰው)።

አበቀለ ግ1. አጎነቆለ፥ አፈጠፈጠ። 2. አቀነቀነ፥ አቆጠቆጠ(ፀጉር)። 3. አበዛ፥ አፈራ። *አገር ሲያረጅ ቋርት ያበቅላል።*

በቀል ስ 1. ቂም። 2. የክፉ ድርጊት ክፉ ምላሽ።

በቀለኛ ቅ ቂመኛ፥ ተበቃይ።

ተበቀለ ግ ቂሙን ተወጣ፥ ለተፈፀመ ክፉ ድርጊት ምላሹን በክፉ ሰጠ።

__በቀል "በቀለ" ስር ተመ.

በቀልቲ "በቀለ"ስር **"በቆልት"**ን ተመ.

በቀልት ዝ.ከ.

በቀረ "ቀረ" ስር ተመ.

በቀር ዝ.ከ.

***በቀቀ**

ተንባቀቀ ግ ተሰነጣጠቀ፥ ተላቀቀ፥ ተከፋፈተ (ከትቻ መሬት በበጋ ወራት)።

እንባቀቀ(እምባቀቀ) ግ አፋጋ፥ አፋሸከ፥ አፉን አለልክ ከፈተ።

በቀቀን ስ መንቆሩ ወደታች ቆልመም ያለና ቀለሙ ደማቅ የሆነ የሰዎችን ንግግርም ሆነ ሌሎች ድምፆችን ማስመሰል የሚችል ወፍ(ስእሉን ወፍ ስር ተመ.)።

በቀበቀ ግ ሰነጠቀ፥ ተረተረ፥ ማረሻውን አጥልቆ አረሰ።

በቀበቅ ስ የተገመሰ፥ የታረሰ መሬት።

ተንበቀበቀ ግ በቅ በቅ አለ፥ እፈ ጠባብ ከሆነ እቃ ውስጥ ውሃ ሲቀዳ (ሲንቆረቆር) የሚሰጠውን

አይነት ድምፅ ሰጠ፤ ተንደቀደቀ።

አንበቀበቀ ግ በቅ በቅ የሚል ድምፅ አሰማ (ለምሳሌ ከቅል ውስጥ ውሃ ሲቀዳ የሚሰማውን የድምፅ አይነት አሰማ)።

በቀተ^1 ግ ነዘነዘ፥ ነተረከ፥ ጨቀጨቀ።

በቀታ(ብቀታ) ስ ንዝነዛ፥ ጭቅጨቃ።

በቀተ^2 ግ ተሰደደ፥ አገር ጥሎ ሄደ።

በቀት ስ ስደት፤ አገር ጥሎ መሄድ።

በቀደም "ቀደመ" ስር ተመ.

በቂ "በቃ" ስር ተመ.

በቃ ግ 1. ልክ፤ በቂ ሆነ (ልብስ፤ ቦታ፤...)። 2.አለቀ፥ ተፈፀመ። *የእርሱ ነገር በቃ*፤ 3. ተሰለቸ፥ ተጠገበ፤ የማያስፈልግ ሆነ። *እስኪበቃው በላ*፤ 4. ደረሰ። *ለትዳር በቃ*፤ 5. ቻለ። *ጥሮ ግሮ ላላማውን ለማሳካት በቃ*፤ 6. ከሃጢአት ነፃ፤ እግዚአብሄር ቀረበው፤ ፍፁም ፃድቅ ሆነ። *ሃጢአተኞች የነበሩም ከብዙ ተጋድሎ በኋላ ሊበቁ ችለዋል*። 7.ቀረ፥ ቆመ፥ ተተወ። *አንደልጅነት ጊዜ መሆን በቃ*፤ 8.የመጨረሻ ውሳኔ መሆኑን ለመግለፅ የሚነገር አባባል። *በቃ አስተሃለሁ / በቃ በዚህ እኔ አልስማማም*።

በቃህ በለው ማረው፤ ይቅር በለው፤ ተወው።

በቃኝ አልሻም፥ አልፈልግም።

ለ __ በቃ ለ __ ደረሰ። *ለትዳር በቃ*።

የበቃ ቅ ፍፁም ፃድቅ የሆነ።

የበቃ የነቃ ያወቀ፥ የተመራመረ።

በቂ(የሚበቃ) ቅ ልክ፤ አጥጋቢ። *ምክንያቱ በቂ ነው*።

በቂ ቅፅል ስ እንደ ስም ሆኖ ሊያገለግል የሚችል ቅፅል። (ለምሳሌ ሟች፥ ገዳይ፤...)።

ብቁ ቅ 1.ተገቢ፤ ተስማሚ ተፈላጊ ችሎታ፣ እውቀት፤...። *ብቁ ባለሙያ*፤ 2. በቂ።

ብቃት ስ 1. ሙሉነት፥ ተገቢነት፥ ተስማሚነት። 2.ፍፁምነት፤ ቅዱስነት።

ብቅት አለ ግ 1. ሰውነቱ ተጎዳ፤ ከሳ። 2. ተዳከመ ፥ ሊሞት ደረሰ።

ተባቃ ግ 1.ተዳረሰ። 2.ለጠብ፥ለኩርፊያ፥ ለመጋደል፤... ደረሰ። *ለዱላ የተባቃነው በርሷ ምክንያት ነው*።

ተብቃቃ ግ ተዳረሰ።

አበቃ ግ 1.ጨረሰ፥ ፈፀመ። 2. ከሳ፤ ደከመ፤ ወደደቀ። 3. አረጀ፤ አፈጀ። 4.አለቀ። *ስራው አበቃ*።

አባቃ ግ 1.አዳረሰ። 2.ለፀብ፤ ለኩርፊያ፥... አደረሰ።

አብቃቃ ግ እንዲበቃ፤ በቂ እንዲሆን አደረገ።

በቅሎ ስ 1.በአባቱ አህያ በእናቱ ፈረስ የሆነ፥ ለጭነት (ሰውን ወይም እቃን ለማጓጓዝ) የሚያገለግል የጋማ ከብት(ስእሉን የቤት እንስሳ ስር ተመ.)። 2.(ዘይ.፥ ስድብ) **ልትወልድ** የማትችል፤ መሃን (ሴት)።

በቅጡ(በቅጥ) "ቅጥ" ስር ተመ.

በቆልት "በቀለ" ስር ተመ.

በቆሎ (ቦቆሎ) ስ በቆላና በወይና ደጋ ሊበቅል የሚችል፥ ቅጠሉ ሾጠጥ ብሎ ርዝመት ያለው፥ ድርብርብ በሆነ ሽፋን ተጠቅልለው የሚገኙ ብዙ ፍሬዎች ያሉት የእህል አይነት፤ የባህር ማሽላ፤ ባርማሽላ። ተክሉም በቆሎ ይባላል።

በቋል(በቋሊ) ስ በእህል ሰብል ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርስ የወፍ አይነት፤ ጥሬ ፈጅ ወፍ፤ ጨረባ።

በተሃ ስ ጌሾ ያልበዛበት ለጋ ጠጅ።

በተለይ "ለየ" ስር ተመ.

በተቀር "ቀረ" ስር **"በስተቀር"**ን ተመ.

በተበተ ግ ቦጠቦጠ፤ ውስጥ ውስጡን በላ፤ ቦተቦተ።

በቶተ ግ አረጀ፥ አለቀ፥ ተቀዳደደ (ልብስ)።

ቡትቶ(ብቱቶ፥ብትቶ) ስ እላቂ፤ ድሪቶ፥ የተቀዳደደ አሮጌ ልብስ።

ቡትቷም ቅ (ስድብ) 1. የተቀዳደደና የተጣጣፈ ልብስ የሚለብስ። 2. (ዘይ.) ዝባዝንኪያም።

በተነ ግ 1.ረጨ፥ ዘራ። 2. ለያየ፥ ለየብቻ አደረገ (በአንድነት የነበረን ነገር)። 3. አባከነ፥ ያለአግባብ አጠፋ (ገንዘብን) ። 4. (ስብሰባን ፥ አድማን፤...)እንዲቆም፤ እንዲቋረጥ፥ እንዲቀር፥... አደረገ።

ብትን ቅ በአንድነት ያይደለ፥ ተለያይቶና ለየብቻ ሆኖ የሚገኝ።

ብትን ድልህ ስ በውሃ ያልታሸ ወይም ያልተሳቆጠ የበርበሬ ዱቄት።

ብትን ጨርቅ ስ ገና ያልተሰፋ በጣቃ ወይም በነዶ ደረጃ ያለ ጨርቅ።

ብትንትኑ ወጣ ተበታተነ።

ተበተነ ግ 1. ተረጨ፥ ተሰራጨ፥ ተዘራ። 2. ተለያየ፥ በየፊናው ሄደ።

ተበታተነ ግ ተበተነ።

በተከ ግ ቆረጠ፥ በጠሰ፤ በጠቀ፥ በሰከ።

ብትክትክ ቅ ቁርጥርጥ፥ብጥስጥስ፥ ብጥቅጥቅ፤ ብስክስክ።

ተብተከተከ ግ 1. ተበጣጠሰ፥ ተበጣጠቀ፥

በአል (ብ.ቁ. **በአላት**) ስ በሳምንት ወይም በወር ወይም በአመት አንድ ቀን የሚከበር፥ ስራ የማይሰራበትና ታርፎ የሚዋልበት ቀን (ለምሳሌ. ሰንበት፥ ጥምቀት፥...የሚውልበት ቀን)።

በአል አከበረ በበአል ምክንያት ስራ ሳይሰራ አርፎ ዋለ።

በአለ__ የ__በአል። *በአለ ልደት።*

የበአል ቀን ስ በበአል ምክንያት ስራ ሳይሰራበት ተከብሮ የሚውል ቀን።

በእንተ(በንተ) በለ። *ምፅዋት ጠያቂው በእንተ ማርያም እያለ ይለምናል።*

በከለ ግ 1. አበላሸ፥ አቆሸሸ፥ አጠፋ (ስምን፥ ልብስን፥ አየርን፥...)። 2. አስተላለፈ፥ አጋባ (በሽታን፥ መጥፎ ባህርይን፥ አስተሳሰብን)።

ብክለ ስ የማበላሸት፥ የማቆሸሽ፥ የማጥፋት ድርጊት።

ተበከለ ግ ተበላሸ፥ ቆሸሸ፥ ጠፋ።

***በከረ**

በኩረሉሚ(በህረ ሉሚ፥ በትረ ሉሚ) ስ ባለሙም ሆነ መልኩ ብርቱካን የሚመስል፥ መጠኑ ከሉሚ በለጥ ከብርቱካን አነስ ያለ የሉሚ አይነት(ስእሉን ፍራፍሬ ስር ተመ.)።

በኩር(በክር፥በህር) ቅ 1. አንጋፋ፥ የመጀመሪያ (ልጅ)። 2. አለቃ፥ ታላቅ፥ ግንባር ቀደም።

በኩራት ስ በኦሪት ህግ መሰረት ለቤተመቅደስ ይሰጥ የነበረ የሰውም ሆነ የእንስሳ የመጀመሪያ ልጅ፥ እንዲሁም መጀመሪያ የደረሰ የሰብል ፍሬ።

ብኩርና ስ 1. በኩር መሆን። 2. ልቅና (አልቅና)።

በካር ቅ ወልዳ የማታውቅና መውለድ የመጀመሪያ ጊዜዋ የሆነ (ሴት)።

ተበከረች ግ ለመጀመሪያ ጊዜ ወለደች።

አበክሮ ተው.ግ. 1. አስቀድሞ፥ ቀደም ብሎ። *ጉዳዩን አበክሮ ነው የነገረኝ።* 2. አጠንክሮ፥ አስተንክሮ።

በከራ[1] ስ ታላቅ የጋሻ አይነት።

በከራ[2] ስ 1.መካከሉ ቀጠን ያለ፥ ጸርዱሩ እንደ እንዝርት ራስ ክብ የሆነ፥ መሃሉ ላይ በክር ታስሮ ወደላይና ወደታች ሲወረውሩት የሚጠቀለልና የሚተረተር የልጆች መጫወቻ። 2. የስፌት መኪና ክር ማጠንጠኛ ወይም ክሩ የሚጠመጠምበት እንጨት።

***በከበከ**

ተንበከበከ ግ ተንደከደከ፥ ፈላ (ለምሳሌ የሽሮ ወጥ፥ የጠላ ድፍድፍ)።

አንበከበከ ግ እንደከደከ፥ አፈላ።

በከተ ግ 1. በሰበሰ፡ ገማ፡ ከረፋ። 2. በጣም ረሰ፡ ረሰረሰ (በውሃ፡ በዝናብ)። 3. አደፈ። 4. ተባርኮ ሳይታረድ ሞተ (ከብት)።

በክት ቅ 1. የጠነባ፡ የበሰበሰ። 2. ሳይባረክ ወይም ሳይታረድ የሞተ (ከብት)። 3. (ስድብ) የማይረባ፡ ደደብ።

በ__በኩል 1. ከስም፡ ከተውላጠ ስም፡…ጋር እየተቀናጀ አቅጣጫን ለማመልከት የሚነገር ቃል። *በታች በኩል/ በቀኝ በኩል*፡…። 2. ከስም፡ ከተውላጠ ስም፡…ጋር እየተቀናጀ ድርሻን፡ ፈንታን፡ ሃላፊነትን ለመጠቆም የሚያገለግል ቃል። *በእኔ በኩል ችግር የለም*።

በኩረ ሎሚ "*በከረ" ስር ተመ.

በኩራት ዝ.ከ.

በኩር ዝ.ከ.

በካር ዝ.ከ.

በከር "*በከረ" ስር "በኩር"ን ተመ.

በክት "በከተ" ስር ተመ.

በወዘ ግ ቀሳቀሰ፡ ደባለቀ።

ብወዛ ስ ማቀሳቀል፡ ማደባለቅ።

በዘበዘ ግ 1. ዘረፈ፡ ገፈፈ፡ ቀማ፡ መዘበረ። 2. አይንን አንፀባረቀ፡ አጥበረበረ፡ አፈዘዘ፡ ማየት ከለከለ።

በዝባዥ ቅ 1. ዘራፊ፡ ቀማኛ፡ ገፋፊ። 2. ሰራተኛው ለሚያፈሰው ላብ ተገቢውን ክፍያ የማይሰጥ፡ በሰራተኛ ጉልበት አላግባብ የሚጠቀም።

ብዝበዛ ስ 1. ዘረፋ፡ ቅሚያ፡ ገፈፋ። 2. የሰራተኛውን ጉልበት ያለ ተገቢው ክፍያ መጠቀም።

ተበዘበዘ ግ ንብረቱን፡ ጉልበቱን ያለአግባብ፡ ያለበቂ ክፍያ ተነጠቀ።

ተበዝባዥ ቅ እንደ ሶሺያሊዝም ርእዮተ ዓለም አመለካከት፡ ለጉልበቱ ዋጋ ተገቢውን ክፍያ ሳያገኝ ለካፒታሊስቱ የሚሰራ፡ ምዝብር፡ ጭቁን።

በዘፈቀደ "ፈቀደ" ስር ተመ.

በዚህ(በይህ) "እዚያ" ስር ተመ.

በዚህም በዚያም ዝ.ከ.

በዚያ ዝ.ከ.

በዛ ግ 1. ከልክ፡ ከመጠን አለፈ፡ በረከተ። 2. ወለደ፡ ረባ።

ሲበዛ 1. በሃይል፡ በጣም፡ ከመጠን በላይ። *ሲበዛ ተናዳጅ ነው*። 2. ከመጠን ሲያልፍ። *ሲበዛ ማርም ይመራል*።

ቢበዛ ቢጠና፡ ግፋ ቢል። *ዋጋው ቢበዛ አስር ብር ቢሆን ነው*።

ብዙ ቅ አያሌ፡ በርካታ።

ብዙሃኑ [ህዝብ] ስ አብዛኛው፡ ሰፊው ህዝብ።

ብዙ ቁጥር ስ (ሰዋ.) ቁጥሩ ከአንድ በላይ ለሆነ ነገር (ስም፡ ቅፅል፡…) የተሰጠ መጠሪያ (ለምሳሌ የመምህር ብዙ ቁጥር መምህራን፡ የክቡር ደግሞ ክቡራን ነው)።

ብዙ ጊዜ ተው.ግ. በተደጋጋሚ።

ብዛት ስ 1.የአንድ ነገር ቁጥር፡ መጠን። 2. አያሌ፡ በርካታ መሆን፡ በቁጥር፡ በመጠን ከፍ ማለት።

ተባዛ ግ 1. ተበራከተ። 2. ተዋለደ፡ በዛ። 3. ሁለት ወይም ከሁለት በላይ ያሉ ቁጥሮች እርስ በርሳቸው ተባዝተው ማስገኘት የሚችሉትን የቁጥር መጠን ያህል እንዲያስገኙ ሆነ። (ለምሳሌ 2X4=8)።

አበዛ ግ 1. አበረከተ፡ ብዙ አደረገ። 2. የማባዛት ስሌት ሰራ።

አበዛው ከመጠን በላይ አደረገ፡ ከገደብ አሳለፈ (ብዙውን ጊዜ መጥፎ ድርጊትን)።

ማብዛት(ማባዛት) ስ 1. ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ቁጥሮች እርስ በርሳቸው ተባዝተው የሚሰጡትን ትልቅ ቁጥር እንዲያስገኙ የሚያደርግ የስሌት መንገድ። ለምሳሌ 3 X 2=6። 2. ከአራቱ የሂሳብ መደቦች የአንዱ መጠሪያ።

የማብዛት(የማባዛት) ምልክት ስ ሁለት ወይም ከሁለት የሚበልጡ ቁጥሮች እርስ በርስ መባዛታቸውን ወይም የሚባዙ መሆናቸውን ለማሳየት በግራ በኩል ከቁጥሮቹ ጎን ወይም በቁጥሮቹ መሃል የሚቀመጥ ምልክት (X)።

አብዛኛው ብዙው፡ ይበልጡ።

አባዛ ግ 1. አንድን ፅሁፍ ወይም ስእል፡…ብዙ ቅጅ ወይም ኮፒ እንዲወጣው አደረገ። 2. አበራከተ፡ ብዙ እንዲሆን አደረገ። 3. አራባ፡ አዋለደ። 4. ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ቁጥሮች እርስ በርሳቸው ተባዝተው የሚፈለገውን ከፍተኛ ቁጥር እንዲያስገኙ አደረገ።

የማባዣ መኪና ስ አንድን ፅሁፍ፡ ስእል፡…እንዳለ ዋናውን አስመስሎ በተፈለገው ብዛት አትሞ የሚያወጣ ወይም የሚያራባ መኪና።

***በዛበዘ**

በዝባዛ ቅ አሰልቺ፡ ነገር ከጀመረ በቶሎ የማይተው (ሰው)።

ተምበዛበዘ ግ ተንዛዛ፡ አሰልቺ ሆነ።

አምበዛበዘ ግ አንዛዛ፡ አሰለቸ፡ አሰልቺ አደረገ።

በዝባዥ "በዘበዘ" ስር ተመ.

በዥድ(በጅድ) ስ ከእምብርት በታች ከብልት በላይ በግራና በቀኝ ያለ የሰውነት ክፍል(በአሉን ሰውነት ስር ተመ.)::

በየ___ በማንኛውም፥ በሁሉም፥ በያንዳንዱ:: *በየቦታው ይታያል::*

በየነ ግ 1. ደነገገ፥ ስርአት አበጀ:: 2. ወሰነ::

በያኝ ቅ ፈራጅ፥ ወሳኝ፥ ዳኛ::

ብያኔ ስ 1. ውሳኔ:: 2. ድንጋጌ፥ ደንብ፥ ስርአት::

ብይን ስ ውሳኔ::

ብይን ሰጠ የቀረበውን የክስ ጭብጥ መርምሮ ሊያስከስስ ወይም ላያስከስስ ይችል እንደሆነ በመለየት ውሳኔ ሰጠ::

አስበየነ ግ አስወሰነ::

በየደ ግ የተሰበረን ወይም የተሸነቆረን ብረት ወይም ብረት ነክ እቃን ቀላጭ ብረት እያፈሰሰ በከፍተኛ የሙቀት ሃይል እርስ በርሱ እንዲያያዝ አደረገ፤ ተከሰ፥ ደፈነ፥ ጠገነ::

በያጅ ስ ብረታ ብረት የሆኑ ነገሮችን እያቀለጠ በማያያዝ፥ በመድፈን፣...የሚሰራ ባለሙያ::

ብይድ ቅ በማቅለጥ የተደፈነ፥ የተበየደ (ብረት ነክ እቃ)::

በያኝ "በየነ" ስር ተመ.

በይበልጥ "በለጠ^1" ስር "በበለጠ" ን ተመ.

በደለ ግ 1. በሌላው ላይ ክፉ ስራ ሰራ፥ ተገቢ ያልሆነ ነገር ፈፀመ:: 2. ጎዳ:: *ላካዚው ተፈጥሮ የበደለው ነው::*

በደለኛ ቅ 1. በሌላው ላይ በደል የፈፀመ፥ ጥፋተኛ፥ ስህተተኛ፥ ግፈኛ፥ በዳይ:: *አምናለሁ በደለኛ ነኝና ይፈረድብኝ::* 2. ተበዳይ፥ በደል፥ ግፍ የተፈፀመበት፥ የተጠቃ፥ የተበደለ:: *በደለኛው እኔ ነኝና ፍረዱብኝ::*

በደል ስ ተገቢ ያልሆነ ስራ፥ ግፍ፥ ጥፋት::

በዳይ ቅ በደል ፈፃሚ::

ተበደለ ግ 1.በደል ተዋለበት:: 2. ተጎዳ::

ተበዳይ ቅ በደል የተፈፀመበት፥ ተጠቂ::

ተባደለ ግ ያንዱ ወገን በዛ የሌላው አነሰ፥ እኩል ለእኩል ሳይሆን ቀረ::

ተባዳላ ስ ያንዱ ወገን በዝቶ የሌላው አነስ ማለት፥ ያለ መመጣጠን:: *ቀርቃባው ተባዳላ ሆኗል::*

***በደረ**

ብድር ስ 1. ለተወሰነ ጊዜ ተጠቅሞ ለመመለስ ከሌላው ዘንድ የሚወሰድ ወይም የተወሰደ ገንዘብ:: 2. በተወሰደው መጠን፥ ተመሳሳዩን ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ለመመለስ ቃል ተገብቶ የሚወሰድና ለራስ ግልጋሎት የሚውል የሌላ ሰው ንብረት (ለምሳሌ እህል):: 3. ውለታ፥ውሮታ፥ በጎ ምላሽ:: 4. ክፉ ምላሽ፥ አፀፋ:: *እንደተበደልኩ ላለቀርም ብድሬን እመልሳለሁ*:: 5.እዳ::

ብድሩን መለሰ 1. ውለታውን ከፈለ:: 2. እዳውን ከፈለ:: 3. ቂሙን ተወጣ፥ ተበቀለ፥ ለተፈፀመው ክፉ ድርጊት አፀፋውን መለሰ::

ብድር ይድረሰው እንደ ስራው ያግኝ፥ ለስራው ስራ አፀፋውን ወይም ተገቢውን ያግኝ::

ብድራት ስ ለተፈፀመ ጥሩ ወይም መጥፎ ድርጊት የሚመለስ ጥሩ ወይም መጥፎ አፀፋ::

ተበደረ ግ 1. ለተወሰነ ጊዜ ተጠቅሞ ለመመለስ ከሌላ ሰው ወሰደ (ለምሳሌ ገንዘብን):: 2. በወሰደው መጠን ያንኑ የሚመስል ለመመለስ ቃል ገብቶ የሌላ ሰው እህል፥...ወሰደ::

ተበዳሪ 1. ለተወሰነ ጊዜ ተጠቅሞ በውለታው መሰረት ለመመለስ የሌላ ሰው ገንዘብ የወሰደ ወይም የሚወስድ:: 2. በወሰደው መጠን ተመሳሳዩን ወይም አይነቱን ለመመለስ ቃል ገብቶ የሌላውን እህል፥...የወሰደ ወይም የሚወስድ:: 3. መበደር የሚያዘወትር::

አበደረ ግ ብድር ወይም በብድር ሰጠ::

አበዳሪ ስ 1.ብድር ወይም በብድር የሚሰጥ (ሰው):: 2. ገንዘብ ያለውና ለሌላ እያበደረ የሚጠቀም::

***በደረገ**

በድረግ(በርደግ) አለ ግ ድንገት አፈፍ፥ ፈጠን ብሎ ተነሳ::

ተበደረገ ግ አፈፍ፥ ፈጠን ብሎ ተነሳ::

***በደበደ**

በድባዳ(በደበድ) ቅ 1. ቀጥቃጣ፥ እርብትብት:: 2. ፈሪ፥ ቡከን::

ተንበደበደ ግ ራደ፥ ተንቀጠቀጠ፥ ፈራ::

አንበደበደ ግ አራደ፥ አንቀጠቀጠ፥ አስጨነቀ::

እንብድብድ ቅ ቀጥቃጣ፥ ፈሪ፥ ቡከን::

በደነ ግ 1. ደነዘዘ፥ ፈዘዘ፥ እንደ በድን ሆነ:: 2. የማይለማ፥ የማይለማ ሬሳ ሆነ፥ ሞተ፥ በድን ሆነ::

በድን ስ 1. ሙት፥ ሬሳ፥ ነፍሱ ከስጋው የተለየች አካል:: 2. (ዘይ.) የደነዘ፥ የፈዘዘ፥ ከሙት የማይሻል::

በዳ ግ (ነውር) ወንድ ሴትን በግብረ ስጋ ተገናኘ::

በዴ ቅ (ነውር) ከተለያዩ ሴቶች ጋር የግብረ

ስጋ ግንኙነት ማድረግ የሚያበውትር::

ብድ ስ (ነውር) የግብረስጋ ግንኙነት ድርጊት::

በዳይ "በደለ" ስር ተመ.

በድባዳ "*በደበደ" ስር ተመ.

በድን "በደነ" ስር ተመ.

በጀ^{1} ግ ረባ፥ ጠቀመ፥ ተሻለ:: *የሚበጀውን ያውቃል::*

በጀ^{2} ግ 1. ደግ፥ መልካም አደረገ:: *በጅተሃል እንኳን መጣህ::* 2. ደግ፥ መልካም፥ ጥሩ ሆነ:: *መምጣትህ በጀ እንጂ ሳትሰማማ ነበር::*

ተበጀ ግ ተሰራ::

ተበጃጀ ግ 1. ተሰራ:: 2. ተጊያጊያጠ፥ ተቆነጃጀ::

አበጀ ግ 1. ሰራ፥ አዘጋጀ:: 2. መልካም፥ ጥሩ፥ ደግ አደረገ:: 3. አፈራ፤ አገኘ:: *ዘመድ አበጅቷል::*

አበጃጀ ግ 1. ሰራ፥ አዘጋጀ:: 2. አሰማመረ፤ አቆነጃጀ::

በጀት(ባጀት) ስ ለስራ ማስኬጃ ወይም ለእቅድ ማስፈፀሚያ የሚመደብ ገንዘብ::

የበጀት አመት ስ ለስራ ማስኬጃ ወይም ለእቅድ ማስፈፀሚያ ተብሎ የሚመደብ ገንዘብ ስራ ላይ ሊውል የሚችልበት የተወሰነ ጊዜ (አንድ አመት)::

በጀድ "በዠድ" ን ተመ.

በጄ እሺ፤ ይሁን::

በጅሮንድ ስ ቀደም ባለው ጊዜ የነበረ የመንግስት ግምጃ ቤት ሃላፊ፤ የገንዘብ ሹም::

በገረ^{1} ግ 1. ለካ፤ መጠነ፤ ምልክት አበጀ፤ ነደፈ:: 2. ቀየሰ፥ መሰረት ጣለ፤ ቆረቆረ፥ ጀመረ::

ቢጋር ስ 1. ንድፍ፥ ምልክት:: 2. ቅያስ፤ ጅምር::

በገረ^{2} ግ ሞከረ፥ ደፈረ::

አይበገርም አይረታም፤ አይሸነፍም::

በገበገ ግ 1. አቃጠለ፤ በላ (እሳት፤ ቁስል):: 2. ገረፈ፥ አሳመመ፤ አቆሰለ::

በገነ ግ 1. ተቃጠለ፥ አረረ፥ ከሰለ:: 2. በጣም ተናደደ፤ ጦፈ::

ብግን ስ አዘውትሮ እሳት ዳር በሚቀመጥ ሰው ቅልጥም ላይ የሚታይ የቆዳ መልክ መቀየርና ጉበት መምሰል፥ መደደር::

ብግናም ቅ (ስድብ) ብግን ያለበት::

አበገነ ግ 1. በጣም አሳመመ፤ አበሰለ:: *ላብግናኝ መጣው::* 2. አናደደ፥ አበሸቀ::

አብግን ቅ አናዳጅ፥ አብሻቂ::

በገና ስ ባለ አስር አውታር (ጅማት) የሙዚቃ መሳሪያ(ስእሉን የሙዚቃ መሳሪያ ስር ተመ.)::

በገና መታ /ደረደረ በገና ተጫወተ::

በገና መቺ(ደርዳሪ) ስ በገና ተጫዋች፤ በገነኛ::

በገነኛ ስ በገና መቺ::

በገፈጅ "በግ" ስር ተመ.

በጋ ስ 1. ከአራቱ አመታዊ ወቅቶች አንዱ የሆነ፥ በመፀውና በፀደይ መካከል ያለ፥ ከታህሳስ 26 እስከ መጋቢት 25 ቀን ድረስ ያለው ፀሃይና ድርቅ የሚበዛበት ወቅት:: 2. ከመስከረም እስከ ግንቦት ያሉትም ዘጠኙ ወራት በተለምዶ የበጋ ወራት እየተባሉ ይጠራሉ::

በግ ስ 1. ስጋው ለምግብ፥ ፀጉሩና ቆዳው ለልብስ የሚሆን፤ የላይ የፊት ጥርስ የሌለው ባረበል የቤት እንስሳ(ስእሉን የቤት እንስሳ ስር ተመ.):: 2. (ዘይ.፥ ስድብ) ሞኝ፤ ቂል፤ የዋህ:: ለ. የዋድቅ ምሳሌ::

በገፈጅ ስ የአንድ በግ ስጋ በአንድ ጊዜ መቀቀል የሚችል ትልቅ ድስት::

በጋማች (በግአማች) ስ በቀድሞ ጊዜ በግ እያረደ ይሸጥ የነበረ የስጋ ነጋዴ::

በጎ ቅ ደህና፤ ደግ፤ ማለፊያ፥ መልካም::

በጎ ሆነ 1.ተሻለው፤ ዳነ፤ ተፈወሰ:: 2. ጥሩ፥ መልካም፥ ደግ ሆነ::

በጎ ምግባር ስ መልካም ስራ፥ ደግኛ ምግባር::

በጎ አድራጊ ቅ ለጋሽ፥ ቸሮታ አድራጊ::

በጎ አድራጎት ስ ድሆችን፤ አቅመ ደካሞችን፥... ለመርዳት የሚደረግ መልካም ስራ::

*በጠለጠለ

ብጥልጣይ ቅ የተበጫጨቀ፤ የተቀደደ::

ብጥልጥል አለ ግ ተብጠለጠለ::

ተብጠለጠለ ግ 1.ተቀዳደደ፥ ተበጫጨቀ:: 2. ስሙ በሃሜት ክፉኛ ጠፋ ወይም ጎደፈ::

አብጠለጠለ ግ 1. ቀዳደደ፤ በጫጨቀ፥ ቀራረጠ:: 2. አማ፤ በሃሜት የሌላውን ስም አጎደፈ::

*በጠረ^{1}

ብጣሪ ስ ከእህል ውስጥ በሰፌድ ወይም በማበጠሪያ ተለይቶ የወጣ አሰር፥ ንፋሽ፥...::

ብጥር ቅ ከቆሻሻው፤ ከንፋሹ ተለይቶ የወጣ፤ የጠራ፥ ጥሩ (እህል)::

ብጥር ያለ ጥሩ፡ ንፁህ፥ እንከን የሌለበት።

ብጥርጥር አደረገ ግ 1. አበጠረ። 2. (ዘይ.) አጣርቶ መረመረ፡ ፈተሸ። 3. ለያየ፥ ብትንትን፥ ግልፅልፅ አደረገ፡ ተነተነ።

ተበጠረ ግ ተነፈሰ፡ ተንጓለለ፥ ተፈላጊው ፍሬ ከአሰር ተለየ።

አበጠረ ግ 1. አነፈሰ፡ አንጓለለ፥ ጥሩውን ከመጥፎው ለየ። 2. (ዘይ.) አጣርቶ መረመረ፡ ፈተሸ።

ማበጠሪያ ስ ማንፈሻ፡ ማንጠርጠሪያ፡ ፍሬን ከገለባ መለያ ሰፌድ ወይም ሌላ ነገር።

*በጠረ^{2}

ተበጠረ ግ በሚዶ ተነቀሰ (ፀጉር)።

አበጠረ ግ ፀጉርን በሚዶ አፍታታ፡ ነቀሰ፡ አሳመረ።

ማበጠሪያ ስ ሚዶ፥ የፀጉር መንቀሻ።

*በጠረረ

በጥራራ(በጠረር) ቅ ኩራተኛ፡ ትእቢተኛ።

ተንበጣረረ(ተንበጠረረ) ግ ተጓደደ፡ ተጀነነ፡ ተኩራራ።

አንበጣረረ(አንበጠረረ) ግ አኩራራ፡ ጀነነ።

በጠሰ ግ ቆረጠ፥ ጎመደ፥ በሰከ፥ በተከ።

በጣሳ ቅ 1. አቅመቢስ፥ በቀላሉ የሚበስክ፥ የሚቆረጥ። 2. (ዘይ.) ኩራተኛ፡ ትእቢተኛ።

ብጣሽ ቅ 1. ጉራጅ፡ ጉማጅ፥ ቁራጭ። 2. ትንሽ። *ብጣሽ ወረቀት ልኮልኝ አያውቅም።*

ብጣሻም ቅ (ስድብ) 1. ጎደሎ፡ ምናምንቴ፥ የማይረባ። 2.(ዘይ.) ያለአቅሙ የሚኩራራ ኩራተኛ።

ብጥስ ቅ የተቆረጠ፡ የተጎመደ።

ብጥስጥስ ቅ 1.ብስክስክ፥ ብትክትክ፡ ቁርጥርጥ። 2. የተቆጻጸደ፥ የተበጫጨቀ፥ እላቂ (ጨርቅ)። 3. ምናምንቴ፡ ቆሻሻ። 4.(ዘይ.) ኩራተኛ፥ ያለአቅሙ የሚምበጣረር።

ብጥስጣሽ ቅ 1.ቁርጥራጭ። 2. ምናምንቴ፡ ቆሻሻ።

ተበጠሰ ግ ተቆረጠ፥ ተጎመደ፥ ተበሰከ፥ ተበተከ።

ተበጣሽ ቅ አቅመቢስ፡ በቀላሉ ሊጎመድ የሚችል።

ተበጣጠሰ ግ 1. ተበታተከ፡ ተበሳሰከ፥ ተጎማመደ። 2. ተበላሸ (ወተት)። 3. (ዘይ.) ተኩራራ፥ ተንቀባረረ።

ተብጠሰጠሰ ግ 1.ተበላሸ(ወተት)። 2. (ዘይ.)ተኩራራ፡ ተንቀባረረ።

አብጠሰጠሰ ግ 1.አኩራራ፡ አንቀባረረ፡ አሞላቀቀ። 2. አብሰከሰከ፥ የአእምሮ እረፍት አሳጣ፡ አቅበዘበዘ።

በጠቀ ግ በጨቀ፥ በጠሰ፥ ቆረጠ፥ በሰከ።

በጣጠቀ ግ በጫጨቀ፥ በጣጠሰ፡ ቆራረጠ፥ በሳሰከ።

ብጥቅጥቅ(ብጥቅጣቂ) ቅ ብጭቅጭቅ፥ ብጥስጥስ።

ተበጣጠቀ ግ ተበጫጨቀ፥ ተበጣጠሰ፡ ተቆራረጠ፡ ተበሳሰከ።

በጠበጠ ግ 1.ደበላለቀ፡ ቀላቀለ፡ አዋሃደ (ድፍድፍን ወይም ሽሮን... ከውሃ ጋር)። 2.አደፈረሰ፡ ጠርቶ ወይም ኩልል ብሎ የነበረውን የምንጭ ወይም የወንዝ ውሃ ከጭቃ ጋር አቀላቀለ። 3. ረበሸ፥ አወከ፡ ፀጥታ ነሳ።

በጥባጭ ቅ አዋኪ፡ አስቸጋሪ፥ ረባሽ።

በጥብጥ ዝ.ክ.

ብጥብጥ ቅ 1. ከውሃ ጋር የተቀላቀለ (ሽሮ ወይም ተልባ)። 2. አዲስ የተሞላና ገና ያልጠራ ወይም ከውሃ ጋር ከተቀላቀለ ብዙም ያልቆየ (የጠላ ድፍድፍ)። 3. ድፍርስ (ውሃ)። 4. ለዳቦ ማንሻነት እንዲሆን በወፍራሙ ተበጥብጦ የሚያድር የእርሾና የትንሽ ዱቄት ድብልቅ።

ብጥ̈ብጥ̈ ስ ንዝንዝ፥ ጭቅጭቅ፥ ሁከት፥ ረብሻ ወይም ግርግር።

ተበጠበጠ ግ 1. ተጠመቀ(ጠላ፥ ጠጅ)። 2. ደፈረሰ፥ ጠሎ የነበረው ጎሽ (ፈሳሽ ነገር)። 3. ታወከ፡ ተረበሸ።

ተበጣበጠ ግ ተጣላ፥ ተረበሸ።

አበጣበጠ ግ አጣላ፥ አረበሸ።

በጠጥ ስ የፍየል ወይም የበግ አይነ ምድር።

በጠጣም ቅ (ነውር፥ስድብ) ፈሪ፡ ቦቅቧቃ።

በጣ ግ ቆረ፥ ሰነጠቀ፥ ሸነተፈ፥ ሰነጠቀ(አካልን)።

ብጥ ቅ የተቆረ፥ ሽንትፍ፥ ሽንትር።

በጣም ተው.ግ. ከቅፅሎችና ከግሶች በፊት እየገባ መልእክቱን የሚያጎላ ቃል። *በጣም ቀይ ነው በጣም ተደሰተ።*

በጣሙን እጅጉን፥ በብዙ፥ በእያሌው። *በጣሙን ደክሟል።*

በጣሳ "በጠሰ" ስር ተመ.

በጥራራ "*በጠረረ" ስር ተመ.

በጥባጭ "በጠበጠ" ስር ተመ.

በጥብጥ ዝ.ክ.

በጨቀ ግ በሰከ፥ በጠሰ፡ ቆረጠ(ጨርቅን፡ ቅጠልን)።

ብጫቂ ቅ ብጣሽ፡ ቅዳጅ።

ብጭቅጫቂ(ብጭቅጭቅ) ቅ ብጥስጣሽ ቁርጥራጭ፥ የተቀዳደደ።

ተበጨቀ ግ ተቆረጠ፥ ተበተከ።

ተበጫጨቀ ግ 1.ተበጣጠሰ፥ ተቀዳደደ። 2. ተቀራመተ፥ ተናጠቀ። *ኣህያይቱን ጅቦች ተበጫጨቋት።*

***በጨበጨ**

በጭባጫ (በጨበጭ፥ብጭብጭ) ቅ 1.የማይጣፍጥ፥ የማይረባ፥ መናኛ(ወጥ፡ ጠላ)። 2. (ስድብ) ፈሪ፥ ቡከን፥ ቦቅቧቃ።

ተንበጫበጨ(ተንበጨበጨ) ግ 1.ጣእም የሌለው፥ የማይረባና መናኛ ነገር ሆነ (ወጥ፡ መጠጥ)። 2. (ነውር) ቀጭን ኣይነ ምድር አስቀመጠው። 3. (ዘይ.) ፈራ፥ ተርበደበደ፥ ከመጠን በላይ ተጨነቀ።

ኣንበጨበጨ ግ 1. ጣእመቢስ፥ መናኛ እንዲሆን አደረገ(ወጥን፡ መጠጥን)። 2. (ነውር) ቀጭን አይነምድር ኣስቀመጠው፡ ቀዘነ። 3. (ዘይ.) ኣስፈራ፥ አርበደበደ።

ኣንበጫበጨ ዝ.ከ.

በፍታ ስ ለስላሳና ስስ የሆነ የጨርቅ ኣይነት።

ቡ የ"በ" ፊደል ካእብ ዘር።

ቡሃ (በሃ፥ቦሃ) ስ 1. እንደቆረቆር፡ ደረመን ያለና ራስ ላይ የሚወጣ፡ ነጭነት ያለው ቁስል። ቅ 2. ራሰ መላጣ።

ቡሃ ሃረግ ስ ግንዱ ነጣ ያለ የሃረግ ኣይነት፥ ሃረግ እራሱ።

ቡሃ ራስ ቅ 1. ራሰ መላጣ፡ በራ። 2. ነጣ ያለ ቆረቆር ወይም ቁስል ያለበት ራስ።

ቡሃ ቁራ ስ ራሱ ላይ ነጭ ምልክት ያለበት፡ ሌላው አካሉ ግን ጥቁር የሆነ ቁራ፥ ኣሞራ።

ቡሃ በግ ስ ግንባሩ ላይ ነጭ ምልክት ያለበት፥ ሌላው አካሉ ግን ጥቁር የሆነ በግ።

ቡሃቃ "ቦካ" ስር ተመ.

ቡሄ ስ ልጆች ጅራፍ አበጅተው የሚያጮሁበት፡ በዋዜማው ችቦ የሚበራበት፥ ሙልሙል ተዘጋጅቶ ለልጆች የሚታደልበት፡ በየኣመቱ ነሃሴ ኣስራ ሶስት ቀን የሚከበር በኣል፥ ደብረታቦር።

ቡሆ "ቦካ" ስር "ቡኮ" ን ተመ.

ቡላ^{1} ቅ 1.ቀለሙ ወይም መልኩ ኣመድ የሚመስል። ስ 2. እመድማ መልክ ያለው (ኣህያ)።

ቡልማ ቅ ኣመድማ።

ቡላ^{2} ስ ከእንሰት የሚዘጋጅ የምግብ ኣይነት።

ቡላድ [ድንጋይ] ስ ሲጋጭ እሳት ሊፈጥር የሚችል የድንጋይ ኣይነት።

ቡልሃ ቅ ምኝ፡ የዋህ።

ቡልቅ

ቡልቅ ኣለ ግ 1.ፍልቅ፡ ቡጥልቅ ብሎ ወጣ፡ ፈሰሰ። 2. በሃይል ወጣ፡ ተፈተለከ፥ በነነ። *መድፉ ሲተኮስ ከኣፈሙዙ ጪስ ቡልቅ ይል ነበር።*

ቡልማ "ቡላ^{1}" ስር ተመ.

ቡልኮ ስ በውፍረትም ሆነ በርዝመት ከጋቢ የሚበልጥ፥ ከጥጥ የሚሰራ ትልቅ ሸማ።

ቡልዶዘር ስ መሬትን እየቆፈረ፡ ድንጋይን እየፈነቀለ ለመጥረግ ወይም ለማፋት የሚያስችል ጠንካራ፥ ወፍራምና ሰፊ የብረት መጋፊያ (ምላጭ) በፊቱ በኩል የተገጠመለት ከባድ ተሽከርካሪ፡ የግንባታ መሳሪያ።

ቡሎን (ቡሉን) ስ ብረቶችን፡ እንጨቶችን፡...ኣንዱን ከሌላው ጋር ለማስተሳሰር የሚያገለግል፡ ከኣንድ ጫፉ በኩል ዙሪያውን ክርክራት ያለው፥ እንደ ወፍራም ምስማር ያለ የብረት ችንካር።

ቡርሽ "ቦረሸ" ስር ተመ.

ቡሩክ(ብሩክ) "ባረከ" ስር ተመ.

ቡራቡሬ "ቡሬ" ስር ተመ.

ቡራከረዩ ኣለ ግ ደነፋ፡ ተቆጣ፡ ያዙኝ ልቀቁኝ ኣለ።

ቡራኬ "ባረከ" ስር ተመ.

ቡሬ ቅ 1.ዝንጉርጉር፥ የነጭና የጥቁር ቀለም ኣይነቶች የተፈነጣጠቀበት ወይም ቀለሞች እየተሰባጠሩ እዚህና እዚያ የሚታዩበት (የቀለም ቅይጥ መልክ)። 2. ቡራቡሬ።

ቡራቡሬ የተለያዩ ቀለማት ድብልቅ ወይም ቅይጥ የሆነ መልክ፥ ዝንጉርጉር።

ቡርቅቅ "ቦረቀቀ" ስር "ቦርቃቃ" ን ተመ.

ቡርቡጭ ኣለ ግ ሞላ ኣለ፡ በመጠኑ ጠገበ (ሆድ)።

ቡርዲ^{1} ስ በላይኛው የሰው ከንፈር በሚገኘው ድድ ላይ ተለጥፎ የሚታይ ድርብና ወፍራም የድድ ስጋ።

ቡርዲያም ቅ ቡርዲ ያለበት።

ቡርዲ^{2} ቅ ፈሪ፥ ቶስቷባ።

ቡሲ(ቡሴ) ስ 1. ጥንካሬ የሌለው፡ ውስጡ ክፍት የሆነ የእፅዋት ኣይነት። 2. (ዘይ.) ኣቅመቢስ፡ ደካማ (ሰው)።

ቡሽ ስ ሲጋቱራ (የእንጨት ፍቅፋቂ) ከመሰለ ነገር የሚሰራ የጠርሙስ፥ የኮዳ፥...ክዳን።

ቡቃ ((ቡኣ) ስ በበገርድ ኣካባቢ የሚሰማ የኣንጀት ህመም ኣይነት።

ቡቃ ወረደው በበገርድ ኣካባቢ የኣንጀት

ህመም ተሰማው።

ቡቃያ "በቀለ" ስር ተመ.

ቡቅሬ (ቡቅሬ+ቡቅር) ስ ጌሾ የሌለውና ያልፈላ ጠላ።

ቡቡ "ባባ" ስር ተመ.

ቡትቷም "በተተ" ስር ተመ.

ቡታ ስ እሪታ፥ ኡኡታ፥ ድረሱልኝ የሚል ጩሀት።

ቡታ ፣ ሰደደ አሪ አለ፤ የደረሰበትን በደል በጩሀት፥ በእሪታ አሰማ፥ ኡኡ አለ።

ቡታ ጋዝ ስ 1. ከነዳጅ ድፍድፍ የሚመረትና መንደድ የሚችል፥ በሲሊንደር ተሞልቶ ለማብሰያ፥ ለመብራት፥...የሚያገለግል ፈሳሽ ጋዝ። 2. በሲሊንደር የተሞላ ቡታጋዝ በቀጭን ቱቦ ተላልፎለት ለማብሰያ የሚያገለግል ምድጃ።

ቡትሌ የ"ብጥሌ"ን 2ኛ ፍቺ ተመ.

ቡትርፍ "ቦተረፈ" ስር ተመ.

ቡትቶ "በተተ" ስር ተመ.

ቡቺ ውሻ የሚጠራበት ስም።

ቡች ቡች አለ ና ና ብሎ ጠራ(ውሻን)።

ቡችላ ስ የአንበሳ ወይም የውሻ፥...ግልገል።

ቡና ስ 1. ተቆልቶ፥ ተወቅጦና ከውሃ ጋር ተፈልቶ የሚጠጣውን ፍሬ የሚያፈራ ተክል፤ ፍሬውም ቡና ይባላል። 2. ከቡና ፍሬ (ተቆልቶ ተወቅጦና ከውሃ ጋር ተፈልቶ) የሚዘጋጅ መጠጥ።

ቡና መፈልፈያ ስ የቡናን ፍሬ ከገለፈቱ ለመለየት የሚያገለግል መሳሪያ።

ቡና ቤት ስ እንደ ቡና፥ ሻይ፥ ለስላሳ፥ የአልኮል መጠጦችና ምግብ የሚሸጥበት የንግድ ቤት።

[የ] ቡና ቁርስ ስ ቡና ሲጠጣ የሚበላ እንደ ቆሎ፥ ቂጣ ያለ ወይም መጠነኛ የሆነ ምግብ።

[የ] ቡና ጀበና ስ ለቡና ማፍያ የሚያገለግል ከሸክላ የተሰራ ጀበና (ስእሉን የሸክላ እቃ ስር ተመ.)።

ቡናማ(ቡኒ) ቅ 1. የደረቀ የቡና ፍሬ ቅርፊት ወይም ጀንፈል ቡና የሚመስል መልክ ያለው። ስ 2. የደረቀ ጀንፈል ቡና የሚመስል የቀለም አይነት።

ቡናኝ "ቦነነ" ስር ተመ.

ቡንኝ ስ በሶስት ወር የሚደርስ የጥቁር ጤፍ አይነት።

ቡአ "ቡቃ" ን ተመ.

ቡክን ቅ ፈሪ፥ እርብትብት።

ቡኬት "ቦካ" ስር ተመ.

ቡክቡካ "ቦከቦከ" ስር ተመ.

ቡኮ "ቦካ" ስር ተመ.

ቡይት ስ ከገንቦ ከፍ ከእንስራ አነስ የሚል የሸክላ እቃ።

ቡዳን ስ በአንድ እጅ ሊዘራ የሚችልና በማረሻ የተበነጠቀ ወይም የተከፈለ የእርሻ መሬት፤ እጣም።

ቡዳ ስ 1. እንደ ህብረተሰቡ ልማዳዊ እምነት፥ ያየውንና ቀልቡ ያረፈበትን ሰው ወይም እንስሳ ለህመም ወይም ለሞት የሚዳርግ መጥፎ አይን ያለው ሰው። ቅ 2. ክፉ። 3. እሱ የሚሰራው ነገር ሁሉ ድብቅ የሆነ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በድብቅ ወይም በምስጢር የሚደረጉ ነገሮች የማያመልጡት (ሰው)።

ቡዳ በላው ቡዳ የሆነ ሰው ስለአየው ታመመ ወይም በጤናው ላይ ጉዳት ደረሰበት።

ቡድስ "ቦደሰ" ስር ተመ.

ቡድን "*ቦደነ^2" ስር ተመ.

ቡጉር "ብጉር" ን ተመ.

ቡግ

ቡግ አለ ግ 1. ተስተካክሉ፥ አምሮና ደምቆ በብዛት በቀለ (ቡቃያ)። 2. ችፍ አለ፥ ግልብጥ ብሎ በብዛት ወጣ (የኩፍኝ፥ የፈንጣጣ፥...ሽፍታ፥ ቁስል)።

ቡግሬት ስ 1. ለጠላ መጥመቂያ የምትሆን እንደ እንስራ ያለች የሸክላ እቃ። 2. እንደ መንቀል ያለች ለመጠጫነት የምታገለግል የሸክላ ዕቃ።

ቡጢ ስ ጡጫ፥ በቅስ፥ የተጨበጠ እጅ።

ቡጥ "ቦጠቦጠ" ስር ተመ.

ቡጥልቅ አለ "*ቦጠለቀ" ስር ተመ.

ቡጥጫ "ቧጠጠ" ስር ተመ.

ቡጫቂ "ቦጨቀ" ስር ተመ.

ቡጭር "ቧጨረ" ስር ተመ.

ቡጭርጭር ዝ.ከ.

ቡጭቅ "ቦጨቀ" ስር ተመ.

ቡጭቅጫቂ ዝ.ከ.

ቡፌ^1 (ቁፌ+ቁፍታ) ስ ለማስተንፈሻነትና ቅቤ መውጣቱን ለማየት የምታገለግል፥ በሚያስፈልግበት ጊዜ ብቻ የምትከፈት፤ ለወተት መናጫ በሚያገለግል እቃ ጎን ላይ የምትገኝ ቀዳዳ፥ ሽንቁሬት።

ቡፌ^2 ስ ብዙውን ጊዜ የምግብ እቃዎችን በውስጡ ለማስቀመጥ የሚያገለግል፤ በጠረጴዛ ወይም በቁምሳጥን ቅርፅ የሚዘጋጅ የቤት እቃ።

ቡፍ

ቡፍ አለ ግ 1. ድምፁ ዝቅ ያለ ጩሀት አሰማ

(ሙሻ)፡፡ 2. ክፍ ሳለ፥ ተነፋ፥ ወደላይ ከፍ፥ ብድግ ላለ (ሊጥ)፡፡ 3. (ዘይ.) የኩርፊያ፥ የቁጣ ገፅታ አሳየ፥ ፊቱን አከበደ፥ አጠቆረ፡፡

ቡፍና ስ 1. ጌሾ የሌለው ቀጭን ጠላ፤ ቡቅሬ፡፡ 2. ያልፈላና ጉሽ የሆነ መናኛ ጠላ፡፡

ቢ የ "በ" ፊደል ሳልስ ዘር፡፡

ቢ__ "ብ-"ን ተመ.

ቢላ^{1} **(ቢላዋ፥ ቢላዎ)** ስ በአንድ ጎኑ ስለት ያለው፥ ለስጋ፥ ለሽንኩርት፥...መቁረጫ፥ መክተፊያ የሚያገለግል የወጥ ቤት እቃ፡፡

ቢላ^{2} ስ በደረቁ ሳር ሜዳ ላይ የሚገኝ እንደ ምርቅ ያለ እሾሀማ ጭንጎት፡፡

ቢላቢሎ "ቢል^{2}" ስር ተመ.

ቢል^{1}

ቢል አለ ግ 1. በቀላሉና በፍጥነት ነደደ፥ ተቀጣጠለ፡፡ 2. (ዘይ.) በጣም ተናደደ፡፡

ቢል^{2}

ቢላቢሎ (ቢሎ) ቅ ስስ (ልብስ)

ቢል አለ ግ በጣም ስስ ሆነ፡፡

ቢል ያለ በጣም ስስ የሆነ፡፡

ቢልቃጥ "ብልቃጥ"ን ተመ.

ቢራ ስ በፋብሪካ ውስጥ ከገብስ ተዘጋጅቶ የሚቀርብ የአልኮል መጠጥ አይነት፡፡

ቢራቢሮ ስ በተለያዩ ህብረቀለማት ያሸበረቁ ክንፎች ያሏት፥ በበጋ ወራት በብዛት የምትታይ የነፍሳት አይነት፡፡

ቢራቢሮ

ቢርካ ስ ቦና ውሃ፡፡

ቢሮ ስ የመንግስት ወይም የድርጅት ወይም የግል ጉዳይን ለማከናወን የሚያገለግል፥ የፅህፈት ስራ የሚካሄድበት ክፍል፥ ቤት፡፡

ቢስ^{1} ስ ቡዳ፥ ክፉ መንፈስ፥ ሰይጣን፡፡

ቢስ አይደይሀ (ምር.) እክፉ ሰው አይን አትንባ፥ ክፉ፥ መጥፎ ነገር አይግጠምሀ፡፡

ቢስ ገላ ስ ደዌ፥ስጋ፤ ቁምጥና፡፡

ቢስ^{2} ቅ ንፉግ፥ ስስታም፡፡

__ቢስ __የሌለው፡፡ *እድለ ቢስ፡፡*

ቢስክሌት "ብስክሌት"ን ተመ.

ቢሻው "ሻ" ስር ተመ.

ቢሽቃጥ ስ ጉጠት፡፡

ቢተዋ ስ በጥንት ጊዜ አርበኛ ወይም ገዳይ ክንዱ ላይ የሚያጠልቀው እንደ አምባር ያለ ጌጥ፡፡

ቢትወደድ ስ ቀደም ባለው ዘመን ለንጉሰነገስቱ እንደቀና አማካሪና ጉዳይ ፈፃሚ ሆኖ ለሚያገለግል ባለሟል ይሰጥ የነበረ የማእረግ ስም፡፡

ቢንጎ ስ ፊደሎችና ቁጥሮች ያሉባቸውን የእጣ ካቦችና የመጫወቻ ካርዶችን በመጠቀምና በአጫዋች የሚሰጠውን ትእዛዝ ቀድሞ በመስራት ተእድለኞች ለጨዋታው የተመደበውን ሽልማት የሚያገኙበትና በርካታ ሰዎች የሚሳተፉበት እንደ ሎተሪ ያለ ጨዋታ(በጨዋታው ቀድሞ ያሸነፈው ጮክ ብሎ "ቢንጎ " ማለትና የታዘዘውን መስራቱን ማስመርመር ይጠበቅበታል)፡፡

ቢኖ "ቪኖ" ን ተመ.

ቢያጆ ስ አንድ ዙር ጉዞ፡፡ *በትልቁ መኪና አስር ቢያጆ ድንጋይ ቢመጫልኝ ላሰብኩት የቤት ስራ ይበቃኛል፡፡*

ቢጃማ "ፒጃማ" ን ተመ.

ቢጋር "በገረ^{1}" ስር ተመ.

ቢጎዲን ስ የሴቶች ፀጉር መጠቅለያ፡፡

ቢጎዲን

ቢጤ(ብጤ) ስ 1. በግብር፥ በጠባይ፥... ተመሳሳይ የሆነ ወይም የሚመስል፡፡ *ቢጤውን ፈልጎ ጓደኛ አበጀ፡፡* 2. እንደ-ያለ፡፡ *ቆሎ ቢጤ አቀብለኝ፡፡*

ቢጫ ቅ 1. የእንቁላል አስኳል ወይም አደይ አበባ የሚመስል፡፡ ስ 2. አደይ አበባ የሚመስል የቀለም አይነት፡፡

ባ^{1} የ "በ" ፊደል ራብእ ዘር፡፡

ባ^{2} በግ ሲጮህ የሚያሰማው የድምፅ አይነት፡፡

ባ አለ ጮሀ (በግ)፡፡

ባ - "ብ-" ን ተመ.

ባህል ስ የህብረተሰብ የአኗኗር ዘዴ፥ ወግ፥ ልማድ፥ እምነት፥...፡፡

የባህል ልውውጥ ስ የየራስን ባህል አንዱ ለሌላው ለማስተዋወቅ በአገሮች መካከል የሚደረግ ግንኙነት፡፡

የባህል ስምምነት ስ በተለያዩ አገሮች መካከል የሚደረግ ባህል ነክ ስምምነት፥ ውል፡፡

ባህላዊ ቅ ባህልን የሚያንፀባርቅ፥ ባህል ነክ የሆነ።

ባህረኛ "**ባህር**^{1}" ስር ተመ.

ባህር^{1} ስ ስፋትና ጥልቀት ያለውና በተወሰነ ቦታ የተከማቸ ውሃ።

ባህሩን ቆርጦ ተሻገረ ባህሩን በዋና አቋርጦ ተሻገረ።

ባህር ነው (ዘይ.) በጣም ሰፊ ነው።

ባህረ ሰላጤ ስ ሾጠጥ ብሎ ወደ መሬት አካል የገባ የባህር ወሽመጥ፥ ምላስ።

ባህረ ሸሽ(ባህር ሸሽ) ስ የባህር ውሃ ተንቶበት ከቆየ በኋላ ትቶት የሄደ መሬት።

ባህረ አረብ (ባህር አረብ) ስ የተለፋና የቀሰመ ሊጥ።

ባህረ ጥምቀት (ጥምቀተ ባህር) ስ 1. የጥምቀት እለት ምእመናን ይጠመቁበት ወይም ይረጩበት ዘንድ በየአመቱ በወንዝ ዳር ወይም አመቺ በሆነ ቦታ ላይ የሚከተር ውሃ፥ ባህር። 2. ከላይ የተጠቀሰው ስነ ስርአት የሚካሄድበትና ታቦት የሚያድርበት ቦታ።

ባህረ ገብ ስ ሾጠጥ ብሎ ወደ ባህር አካል መካከል የተዘረጋ መሬት፤ ልሳነ ምድር።

ባህር መዝገብ ስ ማንኛውም ጉዳይ ወይም ነገር (ንብረት ወይም ገቢና ወጪ፥...) በቋሚነት ተመዝግቦ የሚቀመጥበት ትልቅ መዝገብ።

ባህር ማሽላ (ባር ማሽላ) ስ በቆሎ።

ባህር ማዶ ስ ውጭ አገር።

ባህር ቅል ስ ዱባ።

ባህር ወሳድ ስ የብዙ ልጆች እናት።

[የ] ባህር ዛፍ ስ በዳግማዊ ምኒልክ ጊዜ ፍሬው ከአውስትራሊያ እንዲመጣ ተደርጎ ኢትዮጵያ ውስጥ የለማ፥ የተለያዩ ዝርያዎች ያሉትና በጥቂት አመታት ውስጥ ለአገልግሎት የሚደርስ የትላልቅ ዛፎች አይነት።

የባህር አሞራ ስ ብዙውን ጊዜ በባህር ውስጥ የሚኖሩ ጥቃቅን ነፍሳትን (አሳዎችንና ሌሎችንም) ከባህር ውስጥ እያወጣ የሚመገብ የአሞራ አይነት።

የባህር እቃ ስ እንደ ብርጭቆ፥ ብርሌ፥... የመሳሰሉና በቀላሉ ሊሰበሩ የሚችሉ እቃዎች አይነት።

የባህር ወለል ስ የመሬትን ከፍታ ወይም የውቅያኖስን ጥልቀት ለመለካት እንደ መነሻ ነጥብ ሆኖ ያገለግል ዘንድ በአማካይ የተወሰደ ከውቅያኖስ ውሃ ከላይኛው አካል ጋር ትይዩነት ያለው የመሬት ንጣፍ።

የባህር ወሽመጥ ስ ባህረሰላጤ።

ባህረኛ ስ መርከበኛ።

ባህር^{2} ስ በደቡብና በምእራብ መካከል የሚገኝ የአለም ማእዘን። በተጨማሪ ማእዘንን ተመ.

ባህርይ ስ 1. የአንድ ነገር አፈጣጠር፥ ሁኔታ። 2. የአንድ ነገር ምንነት፥ ሁኔታ። 3. ጠባይ፥ አመል ወይም ግብር።

ባህታዊ ስ ከሰው ተለይቶ እየፆመ፥ እየፀለየና እየሰገደ በዱር በገደል የሚኖር መናኝ፥ ናዝራዊ፥ መነኩሴ።

ባህትውና ስ የባህታዊ ተግባር፥ የአኗኗር ስርአት።

ባለ–

ባለሁለት ስ ማህበረተኞቹን እሁድ የማስተናገድ ተራ የደረሰው፥ ከባለ ሳምንት ቀጥሎ የሚደግስ የፅዋ ጠጪ ማህበረተኞች አባል።

ባለህግ ስ ጋብቻውን ከመሰረቱ ወይም ከጅምሩ በቁርባን ስርአት የፈፀመ ሰው።

ባለመለዮ ስ መደበኛ ወታደር።

ባለመብት ስ 1. የአንድ ነገር ባለቤት።2. ባለጊዜ፥ በጊዜው ስልጣን ወይም ተሰሚነት ያለው ሰው።

ባለሙያ "**ሙያ**" ስር ተመ.

ባለማደሪያ ስ የመንግስት መሬት ተሰጥቶት በእሱ እየተጠቀመ ለመንግስት ግልጋሎት ይሰጥ የነበረ ወታደር።

ባለሟል ስ 1. ከንጉስ ወይም ከታላቅ ባለስልጣን ጋር አብሮ የሚውል፥ አንድን ጉዳይ ለመፈፀምም ሆነ ለማስፈፀም ችሎታ ወይም ተሰሚነትና ተቀባይነት የነበረው ሰው። 2. ቤተኛ፥ የቅርብ ወዳጅና አጋፋሪ።

ባለርስት(ባለመሬት) ስ 1. የራሱ የሆነ የተወሰነ የመሬት ይዞታ ያለው ሰው። 2. የብዙ ወይም የሰፊ መሬት ባለቤት የሆነ፤ የመሬት ከበርቴ።

ባለሰሞን ስ ተራ ሲደርሰው ለስምንት ቀን በቤተክርስቲያን አገልግሎት የመስጠት ሃላፊነት ያለበት ተረኛ ዲያቆን፥ ቄስ፤ ሰሞነኛ።

ባለሳምንት ስ 1. ድግስ ደግሶ የፅዋ ማህበረተኞቹን ለማስተናገድ ተራ ወይም እጣ የደረሰው የማህበሩ አባል። 2. የሚቀጥለው ተረኛ።

ባለስልጣን ስ ስልጣን ያለው ሰው።

ባለስም ስ ዝና፥ ታዋቂነት ያገኘ ሰው።

ባለቀላድ ስ በቀላድ እየተለካ የሚሰጥ መሬት ወይም ርስት የነበረው ሰው።

ባለቅኔ ስ ቅኔ የሚያውቅ፥ ቅኔ የተማረ ሰው።

ባለቤት ስ 1. የአንድ ነገር ባለይዞታ፥ ባለመብት። 2. ባል ወይም ሚስት። የእንግሊ

ባለቤት ለገሊት ናት ወይም የእገሊት ባለቤት ለገሊ ነው። 2. በአንድ አረፍተ ነገር ውስጥ የሚገኘው ግስ ድርጊት በማን ወይም በምን እንደተፈፀመ የሚያመለክትና በአረፍተ ነገሩ መጀመሪያ አርከን ላይ የሚገኝ ቃል ወይም ቃላት።

ባለቤት አከል ስ እንደባለቤት የማዘዝና የመወሰን መብት ያለው ሰው።

ባለተራ "ተራ" ስር ተመ.

ባለተስፋ 1. አገኛለሁ ብሎ በተስፋ የሚጠብቅ። 2. የሚጠብቀውን ነገር የማግኘት ተስፋ ያለው ሰው።

ባለታሪክ "ተረከ" ስር ተመ.

ባለትዳር ቅ ትዳር ያለው ወይም ያላት።

ባለነገር ቅ ክርክር ወይም ሙግት ያለበት (ሰው)።

ባለነጋሪት ስ ነጋሪት የማስጎሸም መብት የነበረው ራስ ወይም ደጃዝማች።

ባለአልጋ ስ የንጉስ ወገን፥ ባላባት፥ ንጉስ።

ባለአጎዛ ስ (ቤ.ክህ.) መምህር፥ አስተማሪ።

ባለእኩል ስ 1. ከተፋታች ንብረት ከባሏ ጋር እኩል የመካፈል መብት ያላት ሴት። 2. ንብረትን ከሌላው ጋር በጋራ የያዘ ሰው።

ባለእዳ ቅ እዳ ያለበት (ሰው)።

ባለእጅ (ባለጅ) ስ (የን.አነ.) ለተለያየ አገልግሎት የሚውሉ የሸክላ እቃዎችን ወይም እንደ ማረሻ፥ ማጭድ ያሉ መሳሪያዎችን የሚሰራ ባለሙያ።

ባለወልድ (በአለ ወልድ) ስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደበትን ቀን ምክንያት በማድረግ በየወሩ በሃያ ዘጠኝ የሚከበር በአል።

ባለወንበር ስ (ቤ.ክህ.) ወንበር ዘርግተው የሚያስተምሩ መምህር።

ባለወግ ስ በቤተክህነት ወይም በቤተ መንግስት ድርጎ ወይም አበል የሚያስጥ የተወሰነ ሹመት ወይም እልቅና የነበረው ሰው።

ባለውለታ "ዋለ^{2}" ስር ተመ.

ባለውቃቢ "ውቃቢ" ስር ተመ.

ባለዝና ስ ስመጥር፥ የታወቀ ሰው።

ባለደም ስ በነፍስ ግድያ ምክንያት ጠላት የተሃየ ሰው።

ባለጅ "ባለእጅ"ን ተመ.

ባለጊዜ ስ 1. ጊዜ ያነሳው፥ ጊዜ የተስማማው፥ ጊዜ የሆነው ሰው። 2. የጊዜው ሹም፥ የጊዜው ባለስልጣን።

ባለ_ ተው.ግ. 1. በመሰለ። *ለከሌና ለከሌ እንዲህ ባለ ነገር ተጣልተዋል / እንዲህ ባለ ወረቀት ላተምም*: 2. በኖረ፥ በነበረ፥በአለ።

ባለቀ ግ አደገ፥ ጎረመሰ፥ ለአቅመ አዳም ደረሰ።

ያልባለቀ ቅ ገና ለአቅመ አዳም ያልደረሰ (ልጅ)።

ባለገ ግ 1. ስርአት የለሸ፥ ህገወጥ፥ ስድ አደግ ሆነ። 2. ከተቃራኒ ፆታ ጋር በስርቆሽ የግብረስጋ ግንኙነት ፈፀመ፥ አመነዘረ።

ባለጌ ቅ ስነስርአት የሌለው፥ ስድ አደግ፥ ያልታረመ።

ብልግና ስ አስነዋሪ ድርጊት።

አባለገ ግ 1. ስነስርአት በሌለው ሁኔታ አሳደገ፥ አስተዳደረ፥...። 2. አማገጠ።

ባለጠጋ(ባለፀጋ) "በለፀገ" ስር ተመ.

ባላ ስ ከላዩ ላይ እቃ ለማንጠልጠል፥ ለመስቀል ወይም ለማውደቅ ያዘመመን አጥር፥ ቤት፥... ለመደገፍ የሚያገለግል ራሱ መንታ የሆነ እንጨት።

ባላባልቾ ስ የወስፈንጥር መስሪያ ባላ እንጨት።

ባላና ደንቆሮ ስ ድር ባላ በሚደራበት ጊዜ፥ ድሩን ለመዘርጋትና ወጥሮ ለመያዝ እንዲያገለግል፤ በድሩ በአንደኛው ጫፍ በኩል የሚተከለው መንትያ ጫፍ ያለው ባላ እንጨትና ሲባል፥ በሁለተኛው ጫፍ በኩል ያለውና ጫፉ መንታነት የሌለው እንጨት በአንድነት የሚጠሩበት ስም።

ባላምባራስ ስ ከግራዝማችነት ዝቅ የሚል የቀድሞ የማእረግ ስም።

ባላባት ስ 1. ጭሰኞች ይገብሩለት የነበረ የአንድ አካባቢ አለቃ፥ ሹም ወይም የመሬት ከበርቴ የነበረ ሰው። 2. ከአያት ከቅድመ አያቱ ጀምሮ የአንድ የተወሰነ አካባቢ ተወላጅ የሆነ እውቅ ሰው።

ባላና ደንቆሮ "ባላ" ስር ተመ.

ባላንጣ ስ 1. ባላጋራ። 2. ይህ የኔ ነው ወይም ለእኔ ነው የሚባለው ባይ፥ ተቀናቃኝ። 3. ተከራካሪ፥ ተወዳዳሪ (ለመብለጥ፥ የበላይ ለመሆን ለማሸነፍ)።

ባላገር (ባለአገር) ስ 1. ገጠር ወይም አገር ቤት። 2. ገጠር ወይም አገር ቤት ውስጥ የሚኖር ሰው። 3.(የን.አነ.) ያልሰለጠነ፥ ቅልጥፍና የሌለው።

ባላጋራ ስ ጠላት፥ ደመኛ።

ባሌስትራ ስ የመኪናውን ሻንሲ የመሸከም ሃይል ያለው ጠንካራና ጠፍጣፋ ደጋንማ ብረት።

ባሌት ስ በንግግር ወይም በዘፈን ሳይሆን በሙዚቃ እየታጀበ በተወዛዋዦች አካላዊ እንቅስቃሴ አማካይነት የሚከናወን ድራማ ወይም የሚተላለፍ የጥበብ ዘርፍ።

ባል ስ ባለ ሚስት፣ ሚስት ያለው ወንድ፤ የሚስት አጣማጅ፣ የትዳር ጓደኛ።

ባልና ሚስት ቀልፍ ስ እርስበርሱ የሚሰካካ፣ የሚገጣጠም የቁልፍ አይነት (ስእሉን ቀልፍ ስር ተመ.)።

ባልቦላ ስ የኤሌክትሪክ ሃይል በመስመር ላይ እንዲተላለፍ ወይም እንዳይተላለፍ ለማድረግ የሚያገለግል፣ ከቆጣሪ ጋር የሚያያዝ የኤሌክትሪክ እቃ።

ባልቴት "በለተተ" ስር ተመ.

ባልትና ስ የቤት አያያዝ፣ የምግብ አዘገጃጀት፣...እውቀት፣ ሙያ፣ ችሎታ።

ባልትናቢስ ቅ (ስድብ) ሙያ ቢስ፣ ሙያ የለሽ።

ባልንጀራ ስ 1.ጓደኛ፤ ምስጢረኛ። 2. ሌብር አደግ፣ እኩያ ወይም አቻ።

ባልደረባ ስ 1. ጓደኛ፤ ባልንጀራ። 2. አባል። *ሰውየው የመስሪያ ቤታችን ባልደረባ ነበሩ።* 3. አጋዥ፣ አገናኝ፣ አስታዋሽ። *ሃላፊው ጉዳዩን ከሰሙ በሂላ ባልደረባ ሰጡኝ።*

ባልደራስ ስ የመንግስት ፈረስና በቅሎ ቤት ሹም፤ አዛዥ።

ባልዲ ስ ለውሃ መቅጃና ማስቀመጫ፤... የሚያገለግል፣ ከብረት ወይም ከፕላስቲክ የተሰራ ባለማንጠልጠያ የቤት እቃ፣ ሽንኪሎ።

ባልጩት ስ እንደ ሻር ወይም እንደ ሴፋሞ ስለት የሚወጣው ድንጋይ።

ባምባ(ባንባ) ስ እንደ ሾላ የሚበላ ፍሬ ያለው የትልቅ ዛፍ አይነት።

ባረቀ ግ 1. በጥንቃቄ ማነስ ወይም በሌላ ምክንያት ሳይታሰብና ሳይፈለግ ድንገት ጥይቱ ተተኮሰ (ጠመንጃ፤ ሽጉጥ)። 2. ሰማይ ጮሀ፤ መብረቅ ተወረወረ። በተጨማሪ **"በረቀ"**ን ተመ.

መብረቅ "በረቀ" ስር ተመ.

ብራቅ ስ መብረቅ።

አምባረቀ (አንባረቀ) ግ 1. እንደ ብራቅ ጮሀ፤ ከፍተኛ ድምፅ አሰማ። 2. አብለጨለጨ፤ ተብለጨለጨ (ሰማይ፤ መብረቅ)።

አባረቀ ግ 1. ሳይታሰብና ሳይፈለግ መሳሪያው ራሱ በራሱ እንዲተኮስ የስህተቱ ምክንያት ሆነ። 2. አምባረቀ።

ባረከ ግ 1. መስቀል አሳለመ። 2. አማተበ። 3. ፀሎት አድርጎ ቀደሰ፤ አነፃ። 4. ጀመረ። 5. የሚበሉ እንስሳትን አንገት ቆረጠ፣ አረደ። 6. አመሰገነ(አምላክን)። 7. መረቀ። 8.ቆረሰ።

ቡራኬ ስ 1. ፀሎት፣ ምስጋና፣ ምርቃት። 2. ለባለ ወግ (ለቄስ፣ ሳቃቢ፣...) የሚሰጥ ተባርኮ የተቆረሰ ትልቅ የዳቦ ቁራሽ።

ቡራኬ ሰጠ ፀሎት አድርጎ ባረከ፣ መስቀል አሳለመ።

ቡሩክ ቅ 1. ጸጋ፣ ምስጉን፣ ትሁት፤ የተመረቀ። 2. የተመሰገነ፤ የተቀደሰ፤ የተከበረ (አምላክ)።

ቡሩክ ሁን (ምር.) የተባረክ፣ የተቀደስክ ሁን።

ተባረከ ግ 1. ዘርማንዘሩ በዛ፣ በረከተ። 2. እድሜ አገኘ፣ ቆየ።

ተባረክ(ምር.) ቡሩክ ሁን።

ባሩድ ስ 1. የቀለሀ ከምሱር፣ በመውጊያ ወይም በመወርወሪያ ሲመታ (ሲወጋ) ፍንዳታና ከፍተኛ ግፊት እንዲፈጠርና ከቀለሁ አፍ ሳይ የተገጠመው የጥይት እርሳስ እንዲተኮስ ወይም ተሰፈንጥሮ እንዲበር የሚያደርግ፣ በቀለሀ ውስጥ የሚሞላ የማእድን ውሁድ። 2. የማእድን አይነት።

ባሪያ(ባርያ) ስ 1. በጦርነት ላይ እየተማረከ ወይም በገንዘብ እየተገዛና እየተሸጠ ወይም ካለበት አካባቢ በግድ ታፍኖ እየተወሰደ ለማራኪው ወይም ለገዛው ወይም አስገድዶ ለወሰደው ሰው በነፃ አገልግሎት ይሰጥ የነበረ ሰው። 2. አገልጋይ፤ ታዛዥ፤ ሎሌ። 3. መብትና ነፃነት የሌለው፤ በተገዥነት የሚኖር ህዝብ። 4 (የን. አነ.) ጥቁር። 5. (ዘይ.) በጣም ጠንካራና ጥሩ አገልግሎት የሚሰጥ (ለእቃ)።

ባርያ ድንጋይ ስ በቀላሉ የማይሰበር፤ ጥቁርና ጠንካራ የሆነ የድንጋይ አይነት።

[ባሪያ] ፈንጋይ ስ የባሪያ ነጋዴ፣ ሰዎችን አፍኖ እያስገደደ ለባርነት ይሸጥ የነበረ ሰው።

የባርያ [አሳዳሪ] ስርአተ ማህበር ስ በህብረተሰብ የእድገት ታሪክ ውስጥ ከጥንታዊው የጋርዮሽ ስርአተ ማህበር ቀጥሎ የመጣ ስርአተ ማህበር።

ባራ ግ አቆመ፣ አባራ (ዝናብ)።

ብራ ስ ዝናብ ያቆመበት ወይም የሌለበት ጊዜ፤ ቀን ወይም ወቅት።

አባራ ግ 1. ዝናብ መጣሉን አቆመ፤ ተወ። 2. (ዘይ.) (መናገሩን፣ መለፍለፉን፤ ማልቀሱን) ተወ፤ አቆመ።

ባሬታ ስ ሽንት መሽኛ፣ መክፈያ፣ ፖፖ።

ባርማሽላ "ባህር ማሽላ" ን ተመ።

ባርባር

ባርባር አለው ፍርሃት፣ ጭንቀት ተሰማው።

ባርኔጣ ስ ለዝናብና ለፀሃይ መከላከያ እንዲሁም ለጌጥ በራስ ላይ የሚደፋ፣ የሚደረግ፡ ከሱፍ ወይም ከጥጥ የሚሰራ ክፍያ።

ባርኔጣ

ባርካ ስ ለማጓጓዣነት የሚያገለግል የጀልባ አይነት።

ባርያ^{1} ስ ራስ የሚያዞርና የሚጥል የበሽታ አይነት።

ባርያ ጣለው የሚጥል በሽታ ኣመመው።

ባርያ^{2} - "ባሪያ" ን ተመ.

ባሮ ሜትር ስ የአየር ግፊት መለኪያ መሳሪያ።

ባሰ ግ 1.አንድ ነገር ከበፊቱ ይልቅ እየጠና፡ እየበረታ ሄደ፡ አየለ (በበጎ ወይም በክፉ መልኩ)። 2. የብስጭት፣ የሃዘን ስሜት ተሰማ። *ሆድ ለባሰው ማጭድ ኣታውሰው*፡ 3.ቸገረ፡ ገደደ። *ምን ባሰህ*፡ 4. ላቀ፣ በለጠ። *ኣንተ ትብስ ኣንተ ትብስ ተባባሉ።*

የባሰ ከበፊቱ የበለጠ፣ የበረታ፣ የጠነከረ።

የባሰ የባሰውን ቀና ቀናውን።

የባሰ ይባስ የፈለገው ይሁን።

ይባስ ብሎ ጭራሹኑ።

ብሶት ስ በአእምሮ ውስጥ ታምቆ የተቀመጠ ችግር፡ በደል፣ ቅሬታ።

ብሶተኛ ቅ ብሶት ያለበት (ሰው)።

ተባባሰ ግ እያየለ፣ እየጨመረ፣ እየከፋ ሄደ።

አባሰ ግ ከበፊቱ ይበልጥ አጠነከረ፣ አበዛ።

ኣብሶ በተለይ፣ በይበልጥ። *ኣብሶ ኣንተ።*

አባባሰ ግ ከበፊተኛው ይበልጥ የከረረ፣ የጠነከረ፣ የከፋ እንዲሆን ኣደረገ።

ባሻገር "ሻገረ" ስር ተመ.

ባቄላ ስ ከኣበባ እህሎች ወገን የሆነ፣ ፍሬው ሞላል ብሎ ተለቅ ተለቅ ያለ፣ ብዙውን ጊዜ በሽሮ፣ በኣሹቅ፣ በንፍሮ፣... መልክ ለምግብነት የሚውል የእህል ኣይነት።

***ባበለ**

ተባበለ ግ ተለመነ፡ ተቆላመጠ፣ ተሸበለበለ።

አባበለ ግ 1.ለመነ፣ ኣቆላመጠ፣ ኣሸበለበለ። 2. ሸነገለ፡ ደለለ።

ማባበያ ስ መሸንገያ፡ መደለያ።

ባቡር ስ ከብረት በሚሰሩ በሁለት ሃዲዶች ላይ የሚጓዝ፣ በድንጋይ ከሰል ወይም በነዳጅ ወይም በሌላ ሃይል ግፊት የሚንቀሳቀስ የመጓጓዣ ኣይነት (ስእሉን መጓጓዣ ስር ተመ.)።

ባቡር መንገድ ስ መኪና ወይም ባቡር የሚሄድበት መንገድ።

ባቡር ጣቢያ ስ የባቡር መነሻና መቆሚያ ቦታ።

[የ]ባቡር ሃዲድ ስ ለባቡር መጓጓዣ ተብሎ ጥርጊያ ይዞ የተዘረጋ የብረት መስመር።

ባቡቲ ስ ከስንዴ ዱቄት የሚዘጋጅ ጥቢኛ፣ ህብስት።

ባባ ግ 1. ራራ፣ ኣዘነ። 2. ፈራ፣ ራደ፣ ተንቀጠቀጠ። 3.ባነነ። 4. የናፍቆት ስሜት ኣደረበት።

ባባ

እንባባ ግ ስረያ የፈለገ ወጠጤ ፍየል እንስቷን በእግሩና በኣፉ እየጓነጠ በመረብሀ ለስረያ ጎተጎተ፣ ኣነባባ።

ቡቡ(ብቡ) ቅ 1. ስጉ፣ የሚፈራ። 2. ኣዛኝ፣ ርህሩህ።

ኣባባ ግ 1. ኣሳዘነ፣ መንፈስን ኣሸበረ። 2. ኣባነነ። 3. ኣስፈራራ።

ባተ ግ ኣዲስ ወር ወይም ኣመት ገባ።

መባቻ ስ የወር መጀመሪያ ወይም መግቢያ (ቀን)።

ኣባተ ግ ጀመረ (ኣዲስ የገባ ወርን)። *መስከረምን የኣባተው ኣገር ቤት ነው።*

ባተለ ግ 1. ብቻውን ለፋ፡ ደከመ። 2. ሚስት ኣልባ ሆነ።

ባተሌ ቅ 1. ኣጋዥ፣ ረዳት የሌለው፡ ብቻውን የሚለፋ። 2. ሚስት የሌለው (ወንድ) ወይም ባል የሌላት (ሴት)።

ባተሉ(ዘባተሎ) ስ ውዳቂ፣ ቡትቶ የሆነ ልብስ፣ ጨርቅ።

ባት ስ ከቅልጥም በስተኋላ፣ በቋንጃና በተረከዝ መካከል የሚገኝ፣ ፍርጥም ያለ የሰውነት ክፍል (ስእሉን ሰውነት ስር ተመ.)።

ባትህን ኣሳየኝ ቶሎ ቶሎ ተራመድ፣ ሂድ።

ባቶ ሁለት ከጉያና ከጭን ኣካባቢ ሰፊ ሆኖ ወደታች ጠበብ እያለ ይወርድና ባት ላይ የሚቆም የሱሪ ኣይነት ።

-ባት "-ብት" ን ተመ.

ባትሪ^{1} ስ በፈሳሽ ወይም በጠጣር መልክ ተዘጋጅቶ ኣስፈላጊውን ሃይል፣ ብርሃን፣ ሙቀት ለመስጠት የሚያገለግል የኤሌክትሪክ ጉልበት ክምችት።

ባትሪ^{2} (የእጅ ባትሪ) ስ አነስተኛ በሆነ እሽግ ውስጥ በተሞላ የኤሌክትሪክ ሃይል (ባትሪ ድንጋይ) የሚሰራ፣ በጨለማ ጊዜ ብርሃን ለመስጠት የሚያገለግል፣ የተለያየ ቅርፅና መጠን ያለው እቃ፤ የባትሪ ቀፎ፣ ሳምባዲና እየተባለም ይጠራል።

ባትሪ

ባትሪ ድንጋይ ስ ለባትሪ(ለእጅ ባትሪ)፣ ለሬዲዮ፣...ተግባር የሚያገለግል፣ በአነስተኛ እሽግ ውስጥ ተከማችቶ የሚገኝ የኤሌክትሪክ ሃይል ወይም ጉልበት።

-ባቸው "-በት" ን ተመ.

-ባችሁ ዝ.ከ.

ባነነ ግ 1. እንቅልፍ ላይ እንዳለ ሰውነቱን በድንጋጤ አንቀሳቀሰ፤ ብትት አለ። 2. ከእንቅልፍ ድንገት ነቃ፤ ተነሳ። 3.(ዘይ.) ዘግይቶ ነቃ፤ አወቀ።

ባና ስ ከበግ ፀጉር የሚሰራ ነጭ ወይም ቀይ ወይም የተለያዩ ቀለማት ያሉት (ዥንጉርጉር የሆነ) እንደብርድ ልብስ የሚያገለግል ወፍራምና ሻካራ የሆነ የሱፍ ልብስ አይነት።

ባንባ "ባምባ" ን ተመ.

ባንክ ስ 1. ጥሬ ገንዘብና እንደ ወርቅ ያሉ ውድ ማእድናት በጥንቃቄ ተጠብቀው የሚቀመጡበት እንደሳጥን ያለ እቃ። 2. ጥሬ ገንዘብን እንደውለታው ወለድ እየከፈለ ወይም ያለወለድ የሚያስቀምጥ ወይም ለደንበኞቹ በወለድ የሚያበድር፣ ልዩ ልዩ ሰነዶችንና ማእድናትን በአደራ የሚያስቀምጥ የአገልግሎት ሂሳብ እያስከፈለ የሃዋላና ሌሎች ተዛማጅ አገልግሎቶችን የሚሰጥ ድርጅት።

የባንክ ኖት ስ በህግ የተፈቀደና ለመገበያያ አገልግሎት የሚውል የወረቀት ገንዘብ።

ባንኮኒ ስ በቡና ቤቶች ውስጥ የቡና ማፍሊያ ማኪናና የአልኮል መጠጥ ጠርሙሶች በተደረደሩበት ቦታ አጠገብ የሚደረግ፣ በውስጡ ቀለል ያሉ እቃዎችን ለመደርደር ወይም ለማስቀመጥ የሚችል፣ በጠረጴዛ ቅርፅ የሚሰራ እቃ።

ባንዲራ ስ በአብዛኛው የተወሰኑና የተለያዩ ቀለማት ካሏቸው ጨርቆች የሚዘጋጅ፣ የአንድ አገር የነፃነት ምልክትና መለያ፣ ሰንደቅ አላማ።

ባንድ ስ በአንድ ቡድን ውስጥ ተደራጅተው የሚሰሩ የሙዚቃ ተጫዋቾች የሚገኙበት አካል።

ባኞ ስ የገላ መታጠቢያ ገንዳ።

ባኞ ቤት ስ የገላ መታጠቢያ ገንዳ የሚገኝበት ክፍል።

ባእድ (ብ.ቁ. **ባእዳን**) ቅ (ሰዋ.) 1. የስጋ ዘመድ ያልሆነ፤ ባዳ። 2. ለአንድ ነገር የራሱ አካል ያልሆነ፤ ሌላ (አካል)።

ባእድ መነሻ ስ (ሰዋ.) መጀመሪያውኑ በስርወ ቃሉ ወይም በአንድ የቃል መነሻ ስር ላይ ያልነበረ፣ በእርባታ ጊዜ ከውልድ ቃል በስተመነሻ በኩል በተቀጣይነት ገብቶ የውልድ ቃሉ አካል ሆኖ የሚያገለግል እስር ምእላድ። *መ-፣ቢ-፣አ-ተ... (ለምሳሌ ሰራ ብሉ - መስሪያ፣ ቢሰራ፣ አሰራር፣...)*

ባእድ መድረሻ ስ (ሰዋ) በስርወ ቃሉ ላይ ያልነበረ፣ ከውልድ ቃል በስተመድረሻ በኩል በተቀጣይነት የሚገባ እስር ምእላድ። *-ያ፣ -ሁ፣... (ለምሳሌ ሰራ ብሉ -መስሪያ፣ ሰራሁ፣...)።*

ባእድ ቋንቋ ስ አገርኛ ያልሆነ የውጪ አገር ቋንቋ።

ባእድ አገር ስ ውጪ አገር።

[የ]ባእድ አገር ሰው ስ የውጪ ዜጋ የሆነ ሰው።

ባእድ ዘር ስ (ሰዋ.) በስርወ ቃሉ ላይ ያልነበረ፣ በእርባታ መንገድ ተፈጥሮ በውልድ ቃል መነሻና መድረሻ ላይ በቅጥያነት ገብቶ፣ የውልድ ቃሉ አካል መስሎ ወይም ሆኖ የሚገኝ እስር ምእላድ። *መ-፣ -ያ፣...(ለምሳሌ ሰራ ብሉ መስሪያ)።*

ባከነ ግ 1. አለቀ፣ ጠፋ(ገንዘብ)። 2. ገንዘቡ ያለአግባብና ያለአላማ እንዲጠፋ፣ እንዲያልቅ ተደረገ። 3. ለፋ፣ ዞረ፣ ደከመ።

ባካና ቅ 1. ገንዘብ የማይበረክትለት፣ የሚያጠፋ። 2. እረፍት የለሽ፣ ባተሌ።

ብኩን ዝ.ከ.

አባከነ ግ 1. ገንዘብን ወይም ሌላ ነገርን ያለአግባብ አጠፋ፣ በተነ። 2. አለፋ፣ አደከመ፣ አዞረ።

አባካኝ ቅ ገንዘብ የማይበረክትለት፣ እጁ ላይ የማይቆይለት፣ ለሚረባውም ለማይረባውም ነገር ገንዘብ የሚያጠፋ።

ተብከነከነ ግ 1. በጣም ተናደደ፣ በቁጭት፣ በንዴት ተቃጠለ። 2. ጠፋ፣ ተድፋፋ፣ አላግባብ አለቀ። 3. ናወዘ፣ ተንከራተተ፣ ለፋ።

አብከነከነ ግ 1.በጣም አናደደ፣ የህሊና እረፍት አሳጣ፣ ቆጨ፣ ከነከነ። 2. አጠፋ፣ አጥፋፋ።

ባክቴሪያ ስ በአይን የማይታይና ረቂቅ የሆነ፥ በአየር፥ በውሃ፥ በአፈር፥ እንዲሁም ህይወት ባላቸው ወይም በሞቱ ነገሮችና በተክሎች ውስጥ የሚገኝ አንዳንዱ ጠቃሚነት ያለው አንዳንዱ ለበሽታ ምክንያት የሚሆን ህዋስ።

ባውሌ ስ ለድር ማድሪያና ለማዳወሪያ የሚያገለግል እንክርት፤ ዋግምበ።

ባዘቀ ግ ተንከረ፥ ተዘፈቀ (በእጃ ወይም በሌላ ነገር)።

ባዘተ ግ 1.በእጁ ፈለቀቀ፥ በጨቀ፥ አፍታታ፥ አለሰለሰ (ጥጥን)። 2.ተፍታታ፥ ተፈለቀቀ፥ ተበጨቀ፥ ለሰለሰ (ጥጥ)። 3. ሳሠ፥ ደቀቀ፥ ድርና ማጉ በን አለ፥ አለቀ (የተዘወተረ ልብስ)። 4. ዛለ፥ ደከመ፥ ላመነ (ሰውነት)።

ባዘቶ ስ የተፈለቀቀ፥ የተበጨቀ፥ የለሰለሰ ጥጥ።

ባዘቶ ገላ ቅ ሰውነቱ ለስላሳ፥ ድንቡሽቡሽ የሆነ።

ብዝት ስ ባዘቶ።

አባዘተ ግ 1. የ"ባዘተ"ን አንደኛ ፍቺ ተመ. 2.(ዘይ.) አማ።

ባዘነ ግ 1. ወዴት እንደሚሄድ ትክክለኛውን መንገድ ስለሳተ ወደሌላ አቅጣጫ ሄደ። 2. ወዲያና ወዲህ ተንከራተተ።

ባዙቃ ስ በትከሻ ላይ የሚያደርጉት፥ ክብደት የሌለው አፈ ሰፊ የጦር መሳሪያ።

ባዛር ስ የተለያዩ ሸቀጣሸቀጦች የሚተዋወቁበትና ረከስ ባለ ዋጋ የሚሸጡበት፥ ብዙውን ጊዜ ለተወሰኑ ቀናት ብቻ የሚቆይ ወይም የሚካሄድ ገበያ።

ባዜቃ ስ ፈሳሽ ሆኖ ክብደት ያለው፥ በባሮሜትር፥ በቴርሞሜትር፥...ውስጥ የሚደረግ ንጥረ ነገር፥ ሜርኩሪ።

ባዝራ ስ ፈረስና በቅሎ የምትወልድ ፈረስ።

ባዝራ ከድንጉል ወለደ አስቀድሞ ሴት ቀጥሎ ወንድ ልጅ ወለደ።

ባይተዋር ቅ ለአካባቢው እንግዳ ወይም አዲስ የሆነ፥ መጤ።

ባዳ "**ባእድ**" ን ተመ.

ባድማ ስ ጠፍ፥ ወና፥ ባዶ ቦታ።

ባድሚንተን ስ ከመረብ ወዲያና ወዲህ በመሆን የላባ ኳስን በራኬት እየመቱ ነጥብ ለማስቆጠር ስልታዊ እንቅስቃሴ የሚታይበት የጨዋታ አይነት፥ የላባ ኳስ ጨዋታ።

ባዶ ቅ 1. ምንም ነገር በውስጡ የሌለበት፥ ወና። ስ 2. ምንም ያለመኖር ሁኔታ።

ባዶውን ቀረ ምንም ሳይዝ፥ ምንም ሳይተርፈው ቀረ።

በባዶ ሆዱ /አፉ ሳይበላ፥ እህል ሳይቀምስ።

ባዶ ለባዶ ዜሮ ለዜሮ። *በሁለቱ ተፎካካሪ ቡድኖች መካከል ምንም አይነት ነጥብ ወይም ውጤት አልተገኘም፤ ባዶ ለባዶ ናቸው።*

ባዶ ራስ የማያስተውል፥ የማያመዛዝን፥ የማያገናዝብ፥ እውቀት የለሽ (ሰው)።

ባዶ ቤት ስ 1. ምንም ነገር (ምግብ፥ መጠጥ ወይም ገንዘብ፥...) የሌለበት ቤት። 2. ሰው የሌለበት ወና ቤት።

ባዶ እጁን ምንም ሳይዝ።

ባዶ እጁን ቀረ ያለ ወገን፥ ያለ ንብረት፥... ብቻውን ቀረ።

ባዶ እግሩን ጫማ ሳያደርግ፥ ያለጫማ።

ባጀ ግ ቆየ፥ ከረመ።

ባጀት "**በጀት**"ን ተመ.

ባጎተ "**ቧገተ**" ን ተመ.

ባጎታ "**ቧገተ**" ስር "**ቧገታ**"ን ተመ.

ባጠጠ ግ ተሞላቀቀ፥ ባለገ።

ባጣጭ ቅ ጥሊቃቂ፥ ባለጌ።

ባጥ ስ የቤት ጣሪያ።

ባጥ አለ ወደላይ አመረ፥ እንጣጥ አለ።

ቤ የ"**በ**" ፊደል ሃምስ ዘር።

ቤርጎ "**አልቤርጎ**" ን ተመ.

ቤሳ ስ እንደ ሳንቲም ያለ የድሮ ገንዘብ።

ቤሳ ቤስቲን የለውም ምንም ገንዘብ የለውም።

ቤሳ ምሳጭ ስ ምሳጭ።

ቤት ስ 1. ከእንጨት ወይም ከድንጋይ ወይም ከጡብ፥... የሚሰራና ለተለያየ አገልግሎት (ለሰው ወይም ለእንስሳት መኖሪያ፥ ለእቃ ማስቀመጫ፥...) የሚውል፥ ዙሪያው በግድግዳ፥ ላዩ በጣሪያ የተከለለ መጠለያ፥ ጎጆ፥ ሳር ቤት፥ ቆርቆሮ ቤት፥ ህንፃ፥...(ስእሉን በሚቀጥለው ገፅ ተመ.)። 2. የትውልድ ወይም የዝምድና ደረጃ፥ ሃረግ። *እኔና አንተ አራት ቤት ነን ወይም የአንድ ቅድመአያት ልጆች ነን ማለት ነው።* 3. የገበጣ መጫወቻ ጉድጓድ። 4. ትዳር። *ልጅህ ቤት ይዟል?* 5. የአሃዞች የአቀማመጥ ደረጃ። *የአንድ ቤት/የአስር ቤት።* 6. የአንድ ነገር ማስቀመጫ፥ መክተቻ፥ ሳጥን። *የክብሪት ቤት።* 7. የግጥም ስንኞች የመጨረሻ ሆሄ። 8. ንግድ ወይም ስራ የሚያካሂድበት ቦታ። ***ንግድ ቤት/ፎቶ ቤት።***

ቤቱ ሞቀ ኑሮው ተሳካ፥ ተሟላ።

ቤቱ ተዘጋ የቤቱ ዋና የነበረው ሰው በሞት ወይም በሌላ ምክንያት ስለተለየ በቤተሰቡ ላይ ችግር መጣ፥ ወደቀ።



ቤት

ቤቱ ፈረሰ 1. ንብረቱ፥ ሃብቱ ተበተነ፥ ባለን ድህነት ላይ ወደቀ። 2. ከትዳር ተፋናቀለ (በፍቺ ወይም በሌላ ምክንያት)።

ቤቱን ሰው አያውቀውም ከቤቱ ሰው ጋብዞ፥ አብልቶ፥ አጠጥቶ አያውቅም።

ቤቱን አሸነፈ ራሱን ችሎ ቤቱን አስተዳደረ፥ ሰርቶ በሚያገኘው የቤቱን ችግር አስወገደ።

ቤቴ ቤቴ አለ ለትዳሩ፥ ለንብረቱ ተጋ፥ አሰበ፥ ተትከረከረ፥ ጣረ።

ቤት ለእንቦሳ አዲስ ቤት ውስጥ የገቡ ሰዎችን ለመጠየቅ የሚሄድ ሰው መልካም ምኞቱን ለመግለፅ የሚያቀርበው የሰላምታ ቃል።

ቤት ለእንግዳ ከቤት ደጃፍ ላይ የቆመን እንግዳ ወደ ቤት ዘለቅ፥ ግባ ለማለት የሚነገር የመጋበዣ ቃል።

ቤት ሙላ (ቤ.ክህ.) ከጉባኤ ቃና ጀምሮ እየተማረ መወድስ ላይ ደረሰ፤ የቅኔ ትምህርቱን አጸረሰ።

ቤት አሳየ መልስ ጠርቶ ጋበዘ (ሙሽሮችን)።

ቤት ከቤቱ ገባ በሃብት፥ በደረጃ ፡ ... ተመሳሳይነት ያላቸው ሰዎች በጋብቻ ተሳሰሩ ወይም ተጋቡ።

ቤት ያፈራው ከቤት ውስጥ ሊገኝ የቻለ ማንኛውም ምግብና መጠጥ።

ቤት ይቁጠረው የችግሩ፥ የመከራው፥ የሚሻ ሰው ብቻ ልክ በትክክል ሊታወቅ አይችልም፤ ስፋት አለው።

[ከ]ቤት (እቤት) ዋለ በህመም ወይም በሽምግልና ምክንያት ከቤት ተቀመጠ፥ ከቤት ለመውጣትና ወዲያ ወዲህ ብሎ ለመስራት አቅም አጣ።

ቤቶች(እዚህ ቤት) ከውጪ የቆመ እንግዳ በቤት ውስጥ ሰው እንዳለና እንደሌለ ለማወቅ ወይም ሰዎቹ ከቤት ውስጥ ብቅ ብለው እንዲያነጋግሩት ሲፈልግ ሰዎቹን የሚጠራበት ቃል።



ቤተልሔም ስ 1. በኢየሩሳሌም የምትገኝ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደባት ቦታ። 2. በቤተክርስቲያን ቅፅረ ግቢ ውስጥ ከቤተክርስቲያኑ በስተምስራቅ በኩል የምትገኝና መስዋእት የሚዘጋጅባት አነስተኛ ቤት።

ቤተመቅደስ ስ 1. የአራት እምነት ተከታዮች ፀሎትና አምልኮ የሚያደርጉበት ቤት። 2. በቤተክርስቲያን ውስጥ የቅዳሴ ፀሎት የሚደርስበት፥ መስዋእት የሚፈተትበት ክፍል፤ መቅደስ።

ቤተመንግስት ስ የአንድ ሃገር መሪ ወይም ርእሰ ብሄር የሚኖርበት የመንግስት ቤት።

ቤተመዘክር ስ ጥንታዊና ታሪካዊ የሆኑ ቅርሶች ተጠብቀው የሚቀመጡበትና በህዝብ የሚጎበኙበት ቤት።

ቤተመዛግብት ስ ልዩ ልዩ ሰነዶችና ፅሁፎች የሚከማቹበትና ተጠብቀው የሚቀመጡበት ቤት።

ቤተመፃህፍት ስ የተለያዩ መፃህፍት የሚገኙበትና አንባቢያን በትውስት ወይም ከውስጡ ገብተው በማንበብ የሚገለገሉበት ቤት።

ቤተምርፋቅ "ረፈቀ" ስር **"ምርፋቅ"** ን ተመ.

ቤተሞገስ ስ የቤተክርስቲያን ወይም የትልቅ ቤት ጉልላት።

ቤተሰብ ስ 1. የስጋ ዝምድና ያላቸው ሰዎች። 2. በአንድ ቤት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች። 3. የሚቀራረቡ፥ የሚተሳሰቡ፥ የሚዋደዱና እንደ ዘመድ የሚተያዩ ጓደኛሞች፥ አብሮ አደጎች።

ቤተሰብ አፈራ ትዳር መሰረተ፥ ልጅ ወለደ።

ቤተሳልገኝ ስ ከጎድን ጋር የተያያዘ የከብት ስጋ ብልት።

ቤተንጉስ ስ ሰቀላ ወይም ሞላላ ያልሆነ ክብ ቤት።

ቤተአምልኮ ስ 1. ሃይማኖታዊ ስነ ስርአት የሚፈፀምበት ቤት። 2. ባእድ አምልኮ የሚፈፀምበት ቦታ፣ ቤት።

ቤተእግዚአብሄር ስ እግዚአብሄር የሚወደስበት፣ የሚመለክበት፣ ሃይማኖታዊ ስነ ስርአት የሚካሄድበት ቤት፣ ቤተ መቅደስ፣ ቤተክርስቲያን፣...።

ቤተክህነት ስ የሃይማኖትና የካህናት አስተዳደር ነክ ስራ የሚካሄድበት ድርጅት፣ መስሪያ ቤት ወይም ቢሮ።

ቤተክርስቲያን ስ የክርስትና እምነት ተከታዮች ለፀሎት፣ ለስግደት፣ ስብከተ ወንጌልን ለመከታተል፣..., የሚሰበሰቡበት፣ ለዚሁ አላማ ተብሎ የተሰራ ቤት፣ ቤተእግዚአብሄር።

ቤተክርስቲያን ሳመ ወደቤተክርስቲያን ሄዶ እጅ ነሳ፣ ሰገደ፣ ተሳለመ፣ ፀሎት አደረገ፣...።

ቤተክርስቲያን ሳሚ ቅ አዘውትሮ ወደቤተክርስቲያን እየሄደ እጅ የሚነሳ፣ የሚሰግድ፣ የሚሳለም፣ የሚፀልይ (ምእመን)።

ቤተክርስቲያን ዘጋ 1. የቤተክርስቲያን አገልግሎት እንዲቋረጥ ወይም እንዳይካሄድ አደረገ። 2. የቤተክርስቲያንን በር በመዝጋት መሃላ ፈፀመ(አላደረግሁም፣ አልፈፀምኩም በማለት)።

ቤተዘመድ ስ ዘመዳሞች፣ የስጋ ዝምድና ያላቸው ሰዎች።

የቤተዘመድ ዳኛ/ጉባኤ ስ የተጣሉ ባልና ሚስትን ወይም ዘመዳሞችን ለማስታረቅ ወይም ለማስማማት የተመረጡ፣ የፍርድ ቤት ድጋፍ ያላቸው የሽምጋይ ዳኞች አካል።

ቤተፀሎት ስ ሃይማኖታዊ ትምህርት የሚሰጥበት፣ ፀሎት የሚደረግበት፣... ቤት።

ቤተፈት ቅ 1. አግኝቶ ያጣ፣ የደሀየ። 2. ትዳሩ የፈረሰ።

ቤት ማያ ስ አዲስ ለተጋቡ ሰዎች የሚደረግ ግብዣ፣ መልስ።

ቤት ሰርሳሪ ስ ዘራፊ፣ ሌባ።

የቤት ልጅ ስ 1. (የን.አነ.) ከቤት አገልጋይ የተወለደ ልጅ። 2. ዘዋሪ ያልሆነ፣ ጨዋና ጭምት የሆነ ልጅ። 3. በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ያደገ የሌላ ሰው ልጅ።

የቤት መኪና ስ ሰዎች በየግላቸው ለመጓጓዣነት የሚጠቀሙበት አነስተኛ መኪና (ስእሉን መጓጓዣ ስር ተመ.)።

የቤት ሰራተኛ ስ በግለሰቦች መኖሪያ ቤት ተቀጥሮ የሚያገለግል ሰው።

የቤት ስራ ስ 1. በመኖሪያ ቤት ውስጥ የሚከናወን እንደ ምግብ ማብሰል፣ ልብስ ማጠብ፣... ያለ ስራ። 2. ተማሪዎች ከትምህርት ሰአት ውጪ ከመኖሪያ ቤታቸው ወስደው እንዲሰሩት የሚሰጣቸው የትምህርት ስራ።

የቤት ስር(ስራ) ስ ከቤት ውስጥ ተፈትሎ የተዘጋጀ ሸማ።

የቤት እመቤት ስ በቢሮ ስራ ወይም በሌላ ከቤት ውጭ በሆነ መተዳደሪያ ላይ ያልተሰማራች ባለትዳር ሴት።

ቤተኛ ቅ እንደቤተሰብ የሚታይ፣ የሚታሰብ ወዳጅ።

ቤንዚን ስ ፔትሮሊየም ከሚባል ድፍድፍ የሚገኝ፣ በፍጥነት የመቀጣጠል ባህርይ ያለውና የተለያዩ ሞተሮችን ለማንቀሳቀስ የሚችል እንዲሁም እንደ ሱፍ ያሉ ልብሶችን በደረቁ ለመጥረግና ለማፅዳት የሚረዳ በፈሳሽ መልክ የሚገኝ ነዳጅ።

ቤዛ ስ 1. አዳኝ፣ መድሃኒት። *ክርስቶስ ቤዛችን ነው።* 2. ዋቢ፣ ሃላፊ፣ መድን። *የገዛሁት ፈረስ ቤዛ አለው።* 3. መከላከያ። *ባርኔጣ የፀሃይና የብርድ ቤዛ ነው።* 4. በካሳ መልክ ወይም እንደምትክ፣ እንደ መለወጫ፣ እንደ መያዣ ሆኖ የሚቀርብ ነገር። *ጠላፊዎቹ ተጠላፊውን የለቀቁት ቤዛ ተቀብለው ነው።*

ቤዠ

ተቤዠ ግ አዳነ፣ ታደገ፣ ቤዛ ሆነ።

ብ የ"በ" ፊደል ሳድስ ዘር።

ብ__ (ከ "ይ" ድምፅ በፊት ሲገባ "ቢ" ፣ ከ "አ" ድምፅ በፊት ሲገባ "ባ" ይሆናል። በሃላፊ ጊዜ በሚነገር ግስ ላይ "በ" ይሆናል)። በግስ መነሻ ላይ እየተቀጠለ ምክንያትን፣ ምኞትን፣ ፀፀትን፣... የሚገልፅና ግስን ከማሰር የሚያስቀር ምእላድ። *ብፈልግ እሄዳለሁ/ ቢመጣም ባይመጣም ቦታው ይዘጋጅ/ ባላገለገልሁ አመሰግናለሁ እንኳ ላልወቀሰም /ሽልማቱን ብተቀበለ ኖሮ ጥሩ ነበር።*

ብሃ "በሃ" ን ተመ.

ብሄር ስ 1. ሃገር። 2. አንድ አይነት ቋንቋ፣ ባህልና ስነልቡናዊ አመለካከት ያለው፣ በታሪክ፣ በኢኮኖሚ፣...የተሳሰረና በተወሰነ ክልል ውስጥ የሚኖር ህዝብ።

ብሄረሰብ ስ ከደም አንድነት ይልቅ በክልል፣ በቋንቋና በባህል አንድነት ላይ የተመሰረተ፣ የተለያዩ ነገዶች የተዋሃዱበት ማህበረሰብ።

ብሄር አቀፍ ቅ አገር አቀፍ።

ብሄራዊ ቅ የሃገር።

ብሄራዊ ወታደር ስ በብሄራዊ ውትድርና አገልግሎት ላይ ያለ ዜጋ።

ብሔራዊ ውትድርና ስ በተወሰነ የእድሜ ክልል ውስጥ ለተወሰነ ጊዜ በውትድርና ተግባር ተሰልፎ አገርን የማገልገል የዜግነት ግዴታ።

ብሔራዊ ጦር ስ በአንድ አገር ውስጥ ከሚገኙ ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የተውጣጣ ሰራዊት።

ብህ "-ብት"ን ተመ.

ብህትውና "ባህታዊ" ስር ተመ.

ብሆር ስ መልኩ በአብዛኛው ድፍርስ ያለ ቢጫ ሆኖ በአይኖቹ ዙሪያ ነጫጭ ፀጉሮች ያሉበት፡ ቀጫጭን ሁነው ወደፊት ቀልበስ ያሉ ቀንዶች ያሉት፡ በብዛት አለትና ቁጥቋጦ በሚገኝበት ተራራማ ስፍራ የሚኖር፡ ሳርና ቅጠላ ቅጠል የሚመገብ የዱር እንስሳ (ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።

ብሽ "-ብት"ን ተመ.

-ብን ዝ.ከ.

ብኝ ዝ.ከ.

ብሉል "በለለ" ስር ተመ.

ብሉይ[ኪዳን] ስ ከኦሪት ዘፍጥረት እስከ ትንቢተ ሚልክያስ ያለው የመፅሃፍ ቅዱስ ክፍል።

ብላሽ "*በለሸ" ስር ተመ.

ብላታ ቅ በቤተመንግስት ውስጥ ለሚያገለግልና ለንጉሱ ዋና ጉዳይ ፈፃሚ ለሆነ ሲቢል ሰው ይሰጥ የነበረ ከበላቴን ጌታ ዝቅ የሚል የማእረግ ስም።

ብላቴና ስ ወጣት ወይም ሴት የሆነ ወይም የሆነች ልጅ።

ብላቴን ጌታ ስ በሚኒስተርነት ደረጃ ላለ ወይም በሌላ ከፍተኛ የስልጣን እርከን ላይ ለደረሰና ዝንባሌው ወደ ስነፅሁፍና ጥናት ለሆነ ሲቢል ሰው ይሰጥ የነበረ ማእረግ።

ብላጊ "በለገ" ስር "ብልግ" ን ተመ.

ብሌን (የአይን ብሌን) ስ የአይን ጥቁሩ ክፍል፡ የአይን ማሚቶ ያለችበት ጥቁር አካል (ስእሉን አይን ስር ተመ.)።

ብል ስ ልብስን፥ ቆዳን፡...የሚበላ፡ የሚበሳ የተባይ አይነት፥ ነቀዝ።

ብልህ ቅ አዋቂ፡ አስተዋይ፡ ዘዴኛ።

ብልሃት ስ 1.እውቀት፥ ጥበብ፥ ዘዴ። 2. ምክንያት፡ ሰበብ። *ያለብልሃት ሊቆር ላይቆርልም።*

ብልሃተኛ ቅ ጥበበኛ፡ ዘዴኛ።

ብልሹ "*በለሸ" ስር ተመ.

ብልሽት ዝ.ከ.

ብልቃጥ(ቢልቃጥ) ስ ለሽቶ ወይም ለቀለም፡...መያዣ የሚሆን አነስተኛ ጠርሙስ።

ብልት "በለተ" ስር ተመ.

ብልዝ "በለዘ" ስር ተመ.

ብልግና "ባለገ" ስር ተመ.

ብልጠት "በለጠ^{2}" ስር ተመ.

ብልጣ ብልጥ ዝ.ከ.

ብልጥ ዝ.ከ.

ብልጫ "በለጠ^{1}" ስር ተመ.

ብልጭልጭ "*በለጨ" ስር ተመ.

ብልጭልጭታ ዝ.ከ.

ብልጭታ ዝ.ከ.

ብልፅግና "በለፀገ" ስር ተመ.

ብሎት "በላ" ስር ተመ.

ብረት ስ 1. የህንፃ መሳሪያዎችን፡ እንደ መጥረቢያ፡ ዶማ፡ ቢላዋ፥... ያሉ ቁሳቁሶችን ለመስራት በጥሬ እቃነት የሚያገለግል ጠንካራ የማእድን አይነት። 2. ጠመንጃ። 3. (ዘይ.) ብረቱ፡ ጠንካራ።

ብረት አውርድ ጠመንጃህን ከትከሻህ ላይ አውርድ የሚል የወታደራዊ ሰልፍ ስነስርአት ትእዛዝ።

ብረት አውጣ ጠመንጃህን ከትከሻህ ላይ አድርግ የሚል የወታደራዊ ሰልፍ ስነስርአት ትእዛዝ።

በብረት ሰላም በል(በብረት ሰላምታ ስጥ) በወታደራዊ የጠመንጃ ሰላምታ አሰጣጥ ደንብ መሰረት ሰላምታ አቅርብ ወይም የሰላምታ ምልክት አሳይ የሚል ትእዛዝ።

ብረት ለበስ ተሽከርካሪ ስ አካሉ በብረት የተሸፈነ ተሽከርካሪ፡ መኪና።

ብረት ማእዘን ስ አናጢዎች፡ ግንበኞች፡... የማእዘን ቅርፅ ለማውጣት ወይም የቅርፁን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የሚለኩበት የማእዘን ቅርፅ ያለው መሳሪያ፡ እስኳድራ እየተባለም ይጠራል።

ብረት ምጣድ ስ ለቡና፡ ለጥራጥሬ መቁያና ለቂጣ መጋገሪያ፡... የሚያገለግል ከብረት የተሰራ ምጣድ።

ብረትቀለም ስ ብረትና ብረት ነክ የሆኑ ነገሮችን ለመቀባት (ለማስጌጥ) የሚያገለግል፥ በቀላሉ የማይለቅ የቀለም አይነት።

ብረት ቀጥቃጭ ስ (የን. አነ.) በገጠር አካባቢ እንደ ማረሻ፥ ቢላዋ፥ ማጭድ ያሉ መሳሪያዎችን ከቤቱ ውስጥ እያዘጋጀ ለተጠቃሚው የሚሸጥ የእጅ ባለሙያ። 2. (ስድብ) ቡዳ፡ ጠይብ።

ብረት ቆብ ስ ከብረት የተሰራ ቆብ፡ የራስ ቁር።

ብረት አቅላጭ ስ ብረት የሚገኝበትን አፈር ወይም ማእድን እየነጠረ የተጣራውን ብረት በማውጣት እንደ ማረሻ፣ ዶማ፣...ያሉ ልዩ ልዩ መሳሪያዎችን የሚሰራ ጥበበኛ።

ብረት ድስት ስ ከብረትና ብረት ነክ ከሆኑ ነገሮች የተሰራ ድስት።

የብረት ቆሎ /አለሎ (ዘይ.) ጠንካራ፣ የማይበገር፣ ጀግና።

የብረት አር ስ የብረት ማእድን ወይም ብረት የሚወጣው አፈር በእሳት እንዲቀልጥ ከተደረገና ብረቱ ተለይቶ ከወጣ በኋላ የሚቀረው ዝቃጭ፣ ጠጣር ጓል።

ብሩህ "በራ" ስር ተመ.

ብሩሽ "ቦረሸ" ስር ተመ.

ብራ "በራ" ስር ተመ.

ብራሪ "በረረ" ስር ተመ.

ብራሮ ዝ.ክ.

ብራቅ "በረቀ" ስር "**መብረቅ**"ን ተመ.

ብራና ስ እንደ ወረቀት ለመፃፊያነት የሚያገለግል የተፋቀና የለሰለሰ የበግ ወይም የፍየል፣... ቆዳ።

ብራና ራስ ስ (በድብ) መላጣ።

ብራኳ ስ ከወገብ በላይ ከማጅራት በታች የሚገኝ የትከሻ አጥንት፣ መጋፊያ።

ብር ስ ውስጠ ክፍት የሆነ የገብስ ወይም የስንዴ፣...እንጻ።

የብር እህል ስ እንደ ገብስ፣ ስንዴ፣ አጃ፣... ያለ የእህል አይነት።

ብረሽሽ ጎላ ብሎ የማይታይ፣ ኮሳሳ ሰው።

ብረሽሽ እህል አገዳው ወይም ብሩ አጠር አጠር ብሎ ፍሬው ጥሩ የሆነ የገብስ ወይም የስንዴ ሰብል።

ብር ስ 1. ገንዘብ። 2. መቶ ሳንቲም ወይም የመቶ ሳንቲም ዋጋ ያለው የወረቀት ገንዘብ። 3. ከአፈር ተነጥሮ የሚወጣ፣ ደረጃው ከወርቅ ቀጥሎ ዝቅ ብሎ የሚገኝ የማእድን አይነት።

ብርአለንጋ ስ 1. እጀታው ከብር የተሰራ አለንጋ። 2. የዘር ስም።

ብርአምባር ስ 1. ከብር የተሰራ አምባር። 2. ክብረንፅህና፣ ድንግልና።

ብርአፍሳሽ ስ ብር እያቀለጠ የተለያዩ ጌጣጌጦችን የሚሰራ የእጅ ባለሙያ።

ብር ጉብጉባት ስ በለምድ፣ በካባ፣ በቀሚስ፣... ጥልፍ ላይ የሚደረግ፣ ልዩ ልዩ ቅርፅ ያለው የብር ጌጥ።

ብርማፋ ጋሻ ስ በብር የተጌጠ ጋሻ።

የብር ኢዮቤልዩ ስ የአንድ ድርጅት 25ኛ አመት በአል።

ብርሃን "በራ" ስር ተመ.

ብርሌ ስ ከአንገቱ ቀጠን ብሎ ከሆዱ ሰፋ የሚል፣ ከብርጭቆ መስሪያ ቁሳቁስ የሚሰራ፣ ለጠላና ለጠጅ መጠጫ የሚያገለግል እቃ።

አፊ ድስት ብርሌ

ሹርቤ ብርሌ

ብርቅ ቅ 1. አዘውትሮ የማይታይ፣ የማይገኝ፣ የማይደረግ ነገር ግን ሲያጋጥም ተወዳጅነት፣ ማራኪነት፣ ተፈላጊነት የሚኖረው። 2. ገና ያልተጠገበ፣ ያልተሰለቸ፣ አዲስ ወይም እንግዳ የሆነ።

ብርቅዬ ቅ 1. ደስ የሚል፣ የሚያምር። 2. ድንቅ።

ብርቅርቅ "በረቀ" ስር ተመ.

ብርባሮ "በረበረ" ስር ተመ.

ብርብራ ስ ፍሬው ወይም ቅጠሉ አሳን አስክሮ ለመያዝ የሚያገለግል የዛፍ አይነት።

ብርቱ "በረታ" ስር ተመ.

ብርታት ዝ.ክ.

ብርቱካን ስ ከሎሚ ከፍ የሚልና ጣእሙ ጣፋጭ የሆነ ውሃ ያለው የፍራፍሬ አይነት። ፍሬውን የሚያፈራው ተክልም ብርቱካን ይባላል።

ብርት ስ ከመዳብ ወይም ከነሃስ የተሰራ የእጅ መታጠቢያ ሳህን።

ብርንዶ[ስጋ] ስ ያልተቀቀለ ወይም ያልተጠበሰ ቀይ ሙዳ፣ ጥሬ ስጋ።

ብርእ "ብእር"ን ተመ.

ብርኩማ^{1} ስ 1. ከእንጨት የሚሰራ ትራስ። 2. በእጆቻቸው እየተመረኮዙ በእንቅቅ የሚሄዱ የአካል ጉዳተኞች እጆቻቸው እንዳይጎዱ እንደ እጅ መጫሚያ የሚገለገሉበት ከእንጨት የሚሰራ አጭር የእጅ መርገጫ። 3. የበገና ወይም የክራር፣... አውታር መደገፊያ፣ መወጠሪያ (ስእሉን የሙዚቃ መሳሪያ ስር ተመ.)።



ብርኩማ [illegible]

ብርኩማ² ስ የበርበሬ ዛላ ቂጥ እንጨት።

ብርኩታ "በረከተ" ስር ተመ.

ብርካቴ "በረከተ" ስር ተመ.

ብርክ "በረከ" ስር ተመ.

ብርክርክ ዝ.ከ.

ብርኮት(ብርጓኔ) ስ ቆዳ የለበሰ የእንጨት ትራስ፤ ብርኩማ።

ብርዝ "በረዘ" ስር ተመ.

ብርድ "በረደ" ስር ተመ.

ብርጉድ ስ ማፋጭ መአዛ ወይም ሽታ ያለው፥ ሴቶች ገላቸውን በጭሱ የሚታጠኑበት የእንጨት አይነት፤ ቡክቡክ።

ብርጌድ ስ 1. በውስጡ የተወሰነ ቁጥር ወይም ብዛት ያላቸውን የጦር አባላት የሚይዝ የአንድ ክፍለ ጦር እግረኛ ክፍል። 2. ለተወሰነ አላማ የተደራጁ ሰዎች የሚገኙበት ቡድን።

ብርግድ "በረገደ" ስር "በርጋዳ" ን ተመ.

ብርጭቆ ስ መስታወት ከሚሰራበት ንጥረ ነገር የሚሰራ ለውሃ፥ ለጠላ፥... መጠጫ የሚያገለግል እቃ።

ብርጭቆ ወረቀት ስ እንደብረትና እንጨት ያሉ ነገሮችን ለመፈግፈግና ለማለስለስ የሚያገለግል፥ አንደኛው ገፁ ለስላሳ ሁለተኛው ደግሞ እንደ አሸዋ የደቀቀ የጠርሙስ ስብርባሪ የተጣበቀበት ሻካራ ወረቀት።

ብሳና (ምሳና) ስ ቅጠሉ ሰፋ ያለና ለስላሳ የሆነ፥ በአብዛኛው ወይናደጋ ላይ የሚበቅል የዛፍ አይነት።

ብሳይ "በሰለ" ስር ተመ.

ብስ "በሳ" ስር ተመ

ብስለት "በሰለ" ስር ተመ.

ብስል ዝ.ከ.

ብስራት "*በሰረ" ስር ተመ.

ብስቁል "በሰቆለ" ስር ተመ.

ብስቁልና ዝ.ከ.

ብስባሽ "በሰበሰ" ስር ተመ.

ብስብስ ዝ.ከ.

ብስና "በሰና" ስር ተመ.

ብስናታም ዝ.ከ.

ብስናት ዝ.ከ.

ብስኩት ስ ዱቄት፥ ውሃ፥ ቅባት፥ ጨው ወይም ስኳር (እንደየአስፈላጊነቱ እንቁላል፥ ወተት ወይም የተለያዩ ቅመማት ሊጨመሩበት ይችላል) ተደባልቆ ከተቦካ በኋላ በስሱ በተለያየ ቅርፅ የሚጋገር የደረቅ ምግብ አይነት።

ብስክ "በሰከ" ስር ተመ.

ብስክሌት ስ በእግር በሚንቀሳቀሱ መዘወሪያዎች አማካይነት ሊሽከረከር የሚችልና ብዙውን ጊዜ ባለ ሁለት ጎማ የሆነ መጓጓዣ (ስእሉን መጓጓዣ ስር ተመ.)።

ብስክስክ "በሰከ" ስር ተመ.

ብስጩ "*በሰጨ" ስር ተመ.

ብስጭት ዝ.ከ.

ብሶተኛ "ባሰ" ስር ተመ.

ብሶት ዝ.ከ.

ብሽ አለ(በሽ አለ) ግ 1. አቅለሸለሸ፥ ቅልብሽ አለ። 2. ድንገት ግልፍ አለ፤ የንዴት፤ የቁጣ ስሜት ተሰማ።

ብሽሽት ስ በጭንና በሆድ መጋጠሚያ ላይ በፍርንጅት አካባቢ የሚገኝ ገላ (ስእሉን ሰውነት ስር ተመ.)።

ብሽቅ "በሸቀ²" ስር ተመ.

ብሽቅጥ "በሸቀጠ" ስር ተመ.

ብቀታ "በቀት" ስር "በቀታ" ን ተመ.

ብቁ "በቃ" ስር ተመ.

ብቃት ዝ.ከ.

ብቅ

ብቅ አለ ግ 1. ወጣ፥ ተገለጠ፥ ታየ። 2. መጣ። *ዛሬ ከየት ብቅ አላችሁ።* 3. ሄደ፥ ደረሰ። *ወደገበያ ብቅ ብዬ እመጣለሁ።*

ብቅ አደረገ ግ አወጣ፥ ገለጠ፥ አሳየ።

ብቅ ጥልቅ አለ ወጣ ገባ አለ።

ብቅ ጥልቅ አደረገ ወጣ ገባ አደረገ።

ብቅል "በቀለ" ስር ተመ.

ብቋያ "በቀለ" ስር "ቡቃያ" ን ተመ.

ብቡ "ባባ" ስር "ቡቡ" ን ተመ.

ብብት(ብብቻ) ስ እጅና ትከሻ ከሚጋጠሙበት ላይ በስተውስጥ በኩል የሚገኝ፥ ከተወሰነ እድሜ በኋላ ለስላሳ ፀጉር የሚበቅልበት የሰውነት ክፍል (ስእሉን ሰውነት ስር ተመ.)።

ብቱቶ "በተተ" ስር "ቡትቶ" ን ተመ.

ብትር "በትር" ን ተመ.

ብትቶ "በተተ"ስር "ቡትቶ"ን ተመ.

ብትን "በተነ" ስር ተመ.

ብትክትክ "በተከ" ስር ተመ.

ብቻ 1. በተናጠል፥ ሌላ ሳይጨመር። *እሱ ብቻ ይምጣ።* 2. ይሁን እንጂ። *የበፊቱን ሂሳብ አልከፈልከኝም፤ ብቻ ለዛሬው አላጠይቅህም።* 3. ቅሬታን፥ አለመርካትን፥...ለመግለፅ የሚያገለግል ቃል። *የተሰጠኝ ርስት የእርሻ አይደለም፤ ብቻ ለሌላ ተግባር ይጠቅም ይሆናል።*

4. ግን:: *ወደማታ እንድትመጣ ብቻ እንዳታመጪ::*

ለየብቻ በተናጠል፣ ለየራስ:: *ለየብቻ መብላት ባገራችን እጅግም ያልተለመደ ባህል ነው::*

ብቻ ለብቻ 1. አንድ ለአንድ:: *ዳዊትና ጎልያድ ብቻ ለብቻ ተፋለሙ::* 2. በተናጠል፣ ለየራስ:: *ብቻ ለብቻ እየመጣችሁ አነጋግሩኝ/ ብርጭቆዎቹ እንዳይሰበሩ ብቻ ለብቻ አስቀምጣቸው::*

የብቻ 1. የግል፣ የራስ:: 2. ልዩ፣ ድንቅ:: *የሱ ቅጥለፋና የብቻ ነው::*

ብቸኛ ቅ 1. ከሌላ ሰው ጋር የማይገጥም፣ ጓደኛ የሌለው:: 2. አንድ በቀል፣ አንድያ:: *ብቸኛ ልጁን ለሞት አሳልፎ ሰጠው::*

ብናኝ "በነነ" ስር ተመ.

ብንቃ ዝ.ከ.

ብእር(ብርእ) ስ ጫፉን ቀለም እያስነኩ ወረቀት ወይም ብራና ላይ ለመፃፍ የሚያገለግል ከመቃ ወይም ከሌላ ነገር የሚሰራ ወይም የተወሰነ የቀለም መጠን በውስጡ የሚይዝና እስከለቀ ድረስ ሳያቋርጥ ሊያስፅፍ የሚችል ጫፈ ብረት የሆነ የፅህፈት መሳሪያ::

የብእር ስም ስ ማንነቱ እንዲታወቅበት የማይፈልግ ፀሃፊ ለህዝብ በሚያቀርባቸው ፅሁፎች ላይ የሚጠቀምበት የምስጢር ስም::

ብከላ "በከለ" ስር ተመ.

ብኩርና "*በከረ"ስር ተመ.

ብኩን "ባከነ" ስር ተመ.

ብክካ "በሃ ድንጋይ" ን ተመ.

ብወዛ "በወዘ" ስር ተመ.

ብው

ብው አለ 1. በሃይል ተቀጣጠለ፣ ነደደ (እሳት):: 2. (ዘይ.) በሃይል ተቆጣ፣ ተናደደ:: 3. ፈነዳ፣ የፍንዳታ ድምፅ አሰማ::

ብው ብሎ ሰከረ በጣም ሰከረ፣ ጥንብዝ አለ::

ብዙ "በዛ" ስር ተመ.

ብዙሃን ዝ.ከ.

ብዙውን ዝ.ከ.

ብዛት ዝ.ከ.

ብዝበዛ "በዘበዘ" ስር ተመ.

ብዝት "ባዘተ"ስር ተመ.

ብዥ

ብዥ አለ ግ ግልፅ ሆኖ በትክክል አልታይ አለ::

ብዥታ ስ በግልፅ ወይም በትክክል ያለመታየት ሁኔታ::

ብያኔ "በየነ" ስር ተመ.

ብይ ስ ብርጭቆ ከሚሰራበት ንጥረ ነገር የተሰራ የተለያየ መልክ (ቀለም) ያለው ድቡልቡል የልጆች መጫወቻ::

ብይን "በየነ" ስር ተመ.

ብይድ "በየደ" ስር ተመ.

ብድ "በዳ" ስር ተመ.

ብድራት "*በደረ" ስር ተመ.

ብድር ዝ.ከ.

ብድግ

ብድግ አለ ግ ከተቀመጠበት ወይም ከተኛበት ተነሳ፣ ቆመ::

ብድግ አደረገ ስ አነሳ::

ብገናም "በገነ" ስር ተመ.

ብገን ዝ.ከ.

ብጉር(ቡጉር) ስ ብዙውን ጊዜ በጉርምስና እድሜ አካባቢ ባሉ ሰዎች ፊት ላይ የሚወጣ፣ ጥቃቅን እትራት ወይም እበጥ መሰል የቆዳ ህመም አይነት::

ብጉንጅ ስ ብዙውን ጊዜ ስስለስ ባለ የሰውነት ክፍል ላይ የሚወጣ እበጥ፣ መግልና ቁስል የሚያስከትል የህመም አይነት::

ብጣሪ "*በጠረ" ስር ተመ.

ብጣሻም "በጠሰ" ስር ተመ.

ብጣሽ ዝ.ከ.

ብጤ "ቢጤ" ን ተመ.

ብጥ "በጣ" ስር ተመ.

ብጥሌ ስ 1. እንጎቻ:: 2. መጠኑ አነስተኛ የሆነ እቃ (ለምሳሌ የቢራ ጠርሙስ)፣ ቡትሌም ይባላል::

ብጥልጣይ "*በጠለጠለ" ስር ተመ.

ብጥር "በጠረ" ስር ተመ.

ብጥስ "በጠሰ" ስር ተመ.

ብጥስጣሽ ዝ.ከ.

ብጥስጥስ ዝ.ከ.

ብጥቅጣቂ "በጠቀ"ስር "ብጥቅጥቅ"ን ተመ.

ብጥቅጥቅ "በጠቀ"ስር ተመ.

ብጥብጥ "በጠበጠ" ስር ተመ.

ብጥብጥ ዝ.ከ.

ብጫቂ "በጨቀ" ስር "ቡጫቂ" ን ተመ.

ብጭቅጫቂ "በጨቀ" ስር ተመ.

ብጭቅጭቅ "በጨቀ" ስር "ብጭቅጫቂ"ን

ተመ.

ብጭብጭ "*በጨበጨ" ስር "በጭባጫ" ን ተመ.

ብዑእ ቅ ክቡር፥ ምስጉን፥ ብሩክ፥ ፃድቅ።

ብፅዓት ስ ስለት፥ የስለት ስጦታ።

ብፅእና ስ መንፈሳዊ ክብር፥ ብፁእነት፥ ቅድስና።

ብሬ ስ ተጋባዡ የፈለገውን እያነሳ እንዲመገብ የተለያዩ የምግብ አይነቶች በተለያዩ እቃዎች ላይ እየተደረጉ ጠረጴዛ ላይ ተደርድረው የሚቀርቡበት የግብዣ አይነት።

ቦ የ "በ" ፊደል ሳብእ ዘር።

ቦሃ "ቡሃ" ን ተመ.

ቦሃቃ "ቡሃቃ"ን ተመ.

ቦለለ^1 ግ ቦነነ፥ ጨሰ (አቧራ፥ ጪስ፥...)።

ቡል አለ(ቡልል አለ) ግ በሃይል ቦነነ፥ ጨሰ።

ቡል ቡል አለ (ቡልል ቡልል አለ) ግ ቡን ቡን አለ፥ ተትጎለጎለ፥ ጨሰ።

ተንቧለለ ግ በሃይል ጨሰ፥ ጪሱ ወደላይ ተነሳ፥ ተትጎለጎለ።

ቦለለ^2 ግ ቦላሌ፥ ሰፊ ሆነ።

ቦላሌ[ሱሪ] ስ ከወገብ በታች እስከ መጫሚያ አካባቢ የሚደርስና ሰፊ የሆነ ሱሪ፥ የቀምጣ ሱሪ ተቃራኒ።

ተንቧለለ ግ 1. ሰፋ፥ ቦላሌ ሆነ። 2. ሰፊ ልብስ (ቀሚስ) ለብሶ በዙር ተሽከረከረ።

***ቦለቦለ**

ቦለቦል(ቦልቧላ) ቅ ተግባቢ፥ ተጫዋች፥ በረበር።

ተንቦለቦለ ግ 1. በብዛት ወረደ፥ ፈሰሰ (ፈሳሽ)። 2. በብዛት ወጣ፥ ተትጎለጎለ (ጪስ)።

አንቦለቦለ ግ 1. አንዶለዶለ፥ በብዛት አፈሰሰ። 2. በሰፊው አወራ።

ቦለደ ግ 1. እንጨትና እንጨትን በማፋጨት፥ ድንጋይና ድንጋይን በማጋጨት እሳት እንዲፈጠር አደረገ፥ እሳቱ አወጣ። 2. (ዘይ.) ፋኖ፥ በረሀኛ ሆነ፥ ሸፈተ።

ቦለድ(ቦለዶ) ቅ 1. ከጅረው (ከወገኖቹ) ተለይቶና ለብቻው ተሰማርቶ የሚታይ (ዝንጀሮ)። 2. (ዘይ.) ቤቱን ለቆ፥ ከህዝብ ለየት ብሎ ጫካ ለጫካ የሚዞር (አጋሚዶ፥ ሽፍታ)።

ቦሊንግ ስ ትልቅነትና ክብደት ያለውን ኳስ ከጣውላ በተሰራ ወለል ላይ በማሽከርከር፥ በጠርሙስ ቅርፅ የተሰሩና በወለሉ ጫፍ የተደረደሩ አስር እንጨቶችን በመጣል የሚደረግ ጨዋታ።

ቦላሌ "ቦለለ^2" ስር ተመ.

ቦልቧላ "*ቦለቦለ" ስር "ቦለቦል"ን ተመ.

ቦምብ ስ የተለያየ መጠንና ቅርፅ ያለው፥ ሲፈነዳ በሰውም ሆነ በንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል አደገኛ የጦር መሳሪያ አይነት።

በቦምብ ደበደበ በተወሰነ ነገር ወይም ቦታ ላይ ቦምብ በተደጋጋሚ በመወርወር ወይም ከአየር በመጣልና በማፈንዳት አደጋ አደረሰ።

ቦምብ ጣለ በቦምብ መታ፥ ቦምብ ወረወረ።

ቦምብ ጣይ አይሮፕላን ስ በተወሰነ ኢላማ ላይ ቦምብ ከአየር ለመወርወር የሚያገለግል የጦር አይሮፕላን።

ቦረሸ ግ በቡርሽ ጠረገ፥ አፀዳ።

ቡርሽ(ብሩሽ) ስ ከፀጉር ወይም ከፕላስቲክ የሚሰራ ቀለም ለመቀቢያ፥ ልብስ ለመጥረጊያ፥ ጠርሙስ ለማጠቢያ፥...የሚያገለግል እቃ።

ተቦረሸ ግ በቡርሽ ፀዳ፥ ተጠረገ።

ቦረቀ ግ ፈነጨ፥ ፈነጠዘ፥ ዘለለ።

ቡረቃ ስ ፍንጠዛ፥ የደስታ ዝላይ።

***ቦረቀቀ**

ቦርቃቃ(ቡርቅቅ) ቅ በጣም የሰፋ፥ የተንቧለለ። *ቦርቃቃ ሱሪ።*

ተንቦረቀቀ ግ አለቅጥ ሰፋ፥ ተንቧለለ።

አንቦረቀቀ ግ አለቅጥ ሰፊ አደረገ፥ አንቧለለ።

ቦረቦረ ግ 1. በመሮ ወይም በመቆፈሪያ፥... በመፈልፈል አጎደጎደ(እንደ ግንድ፥ አለት፥ መሬት፥...ድፍን የነበረን ነገር)። 2. ሸረሸረ (ጎርፍ መሬትን)። 3. ሞረሞረ (የረሃብ ስሜት)። 4. ቀስ በቀስ ውስጥ ውስጡን እየጎዳ አደከመ።

ቦረቦር ቅ 1. ቀዳዳ ያለውና ፍርክስ ፍርክስ የሚል (የአፈር አይነት)። 2. (ዘይ.) ገራም፥ የዋህ የሆነ (ሰው)።

ቦርቧራ ቅ (ዘይ.) ገራም፥ የዋህ፥ ተንኮል የሌለው (ሰው)።

ተቦረቦረ ግ 1. ጎደጎደ፥ ተሸረሸረ፥ ተበላ። 2. ሃይሉ ቀስ በቀስ ውስጥ ውስጡን እየተቀነሰ ሄደ።

ቦረቦጭ ስ የተለያየ ቀለም ያለውና ብርጭቆ የሚመስል የድንጋይ አይነት።

ቦረንትቻ ስ ለአድባር፥ ለቆሌ ተብሎ የሚታረድ ከብት፥ የሚጋገር ቂጣ፥...።

ቦራ ቅ ግንባሩ ላይ ነጭ ፀጉር ያለው (ፈረስ፥ በሬ ወይም ላም)።

ቦርማ(ቦሩማ) ገ.ከ.

ቦርሳ ስ ከቆዳ ወይም ከፕላስቲክ የሚሰራ፣ የተለያየ መጠን ያለው ለገንዘብ ወይም ለአንዳንድ እቃዎች መያዣ የሚያገለግል እቃ።

ቦርቦርቲ ስ የብረት ቆብ፣ የራስ ቁር።

ቦርቧራ "ቦረቦረ" ስር ተመ.

ቦርዴ ስ በጠላ መልክ በወፍራሙ የሚዘጋጅ፣ ጌሾ የማይገባበት የመጠጥ አይነት።

ቦርጭ ስ ወደውጪ ዘርጠጥ ብሎ የሚታይ የሆድ ውፍረት፣ ቀፈት።

ቦርጭ አወጣ ሆዱ ተንዘረጠጠ፣ ቀፈታም ሆነ።

ቦርጫም ቅ ሆደ ዘርጣጣ።

ቦቀልት "በቀለ" ስር "በቆልት"ን ተመ.

ቦቀረ ግ 1. መሃሉን ቀንብቦ የራስ ፀጉርን በመላጨት ሳዱላ ወይም ጋሜ አወጣ። 2. ማሳን አለፍ አለፍ እያለ በማረሻ ተለመ። 3. በአንድ ማሳ ላይ ከተዘራው እህል ውስጥ የደረሰ የደረሰውን ብቻ አለፍ አለፍ እያለ አጨደ።

ቡቅራት ስ 1. መሃል ራስን መላጨት። 2. መሃሉ ላይ የተላጨ የራስ ፀጉር።

ቦቀሰ ግ በቦቅስ መታ።

ቦክስ(ቦቅስ) ስ 1. ቡጢ፣ የተጨበጠ እጅ። 2. (ስፖ.) የራሱ የሆነ የአጨዋወት ህግና ስርአት ያለው፣ በተወሰነ የቦታ ክልል ወይም መድረክ ላይ ጓንት ባጠለቁ ሁለት ተጋጣሚዎች መካከል የሚካሄድ በቡጢ የመደባደብ ውድድር።

ቦክሰኛ(ቦቅሰኛ) ቅ 1. በቦቅስ የሚማታ፣ የሚደበድብ። 2. በቦቅስ ስፖርት ትምህርት የሰለጠነና በዚሁ ሙያ የሚተዳደር ስፖርተኛ።

***ቦቀቦቀ**

ቦቅ ስ ሳያቋርጥ ለረጅም ጊዜ የሚጥል ዝናም የሚያስከትለው ፍሳሽ።

ቦቅቧቃ(ቦቀቦቅ) ቅ ፈሪ፣ ቡከን።

ተንቦቀቦቀ ግ 1. በብዛት ወረደ፣ ፈሰሰ (ውሃ፣ ጎርፍ)። 2. በጣም ፈራ።

አንቦቀቦቀ ግ 1. በሃይል ዘነመ፣ ረዘም ላለ ሰአት ሃይለኛ ዝናም ጣለ። 2. አስፈራራ።

እምቡቅቡቅ ቅ ፈሪ፣ ቡከን።

ቦቃ ቅ ግንባሩ ላይ ነጭ ፀጉር ያለው (ከብት)።

ቦቅማ ዝ.ክ.

ቦቅ "*ቦቀቦቀ" ስር ተመ.

ቦቅስ "ቦቀሰ" ስር ተመ.

ቦቅቧቃ "ቦቀቦቀ" ስር ተመ.

ቦቆሎ "በቆሎ"ን ተመ.

ቦተረፈ ግ በሃይል በጫቀ፣ ዘነጠለ።

ቡትርፍ ቅ ቡጭቅ።

ተቦተረፈ ግ ተበጫቀ፣ ተዘነጠለ።

ቦታ ስ 1. ስፍራ፣ የተወሰነ አካባቢ፣ ክልል። 2. ይዞታ (የመሬት)። 3. መገኛ፣ መኖሪያ፣ መቀመጫ። 4. መሰማሪያ (የስራ)። 5. ደረጃ፣ ማእረግ(የስልጣን)።

ቦታ ለቀቀ 1. የነበረበትን ስፍራ ተወ። 2. ከነበረበት ስፍራ ተነሳ፣ ተወገደ።

ቦታ ሰጠ 1. አስቀመጠ። *ለእንግዶቹ ቦታ ሰጣቸው።* 2. ከቁም ነገር ቦታ አገባ። *ላንተ ልፍለፋ ማን ቦታ ይሰጠዋል።*

ቦታ ያዘ ተቀመጠ፣ ተደላደለ።

ቦታ ቦታ አለው ለሁሉም ነገር ጊዜ፣ ሁኔታ፣ ዘዴ፣ አጠቃቀም፣ አፈፃፀም አለው።

ቦታ ቦታውን ያዘ እንደየአግባቡ ተቀመጠ፣ ተደላደለ።

ቦት ስ ከቆዳ ወይም ከፕላስቲክ፣… የሚዘጋጅ እስከ ባት ድረስ የሚሸፍን ረጅም ጫማ።

ቦነነ ግ 1. ጨሰ፣ በነነ። *ሲጋራው ቦነነ።* 2. ሳሳ፣ ደቀቀ፣ አለቀ፣ በነነ። *ተዘውትሮ ከመለበሱ የተነሳ ሱሪው ከጉልበቱ ላይ ቦነነ።*

ቡናኝ "በነነ" ስር "ብናኝ"ን ተመ.

አቦነነ ግ 1. አጨሰ፣ አበነነ (ጨሰን፣ አቧራን፣…)። 2. ጨረሰ፣ አበነነ(ልብስን)። 3. ጨረሰ፣ ፈፀመ(ስራን)። 4. በሃይል መታ፣ አዘረጠ። *በሽመል አቦነነው።*

ቦና ስ ዝናም፣ ልምላሜ የሌለበት ወቅት፣ ድርቅ።

የቦና ጥጃ ስ በድርቅ ምክንያት የተጎዳ ወይም የከሳ ጥጃ።

ቦኖ ስ በሆቴል ቤቶች፣ በሻይ ቤቶች፣… የሽያጭንና የግዢን ሁኔታ ለመከታተያ እንዲያገለግል ከፕላስቲክ፣ ከቆርቆሮ፣… የሚዘጋጅ የገንዘብ ምትክ።

[የ]ቦኖ ውሃ ስ በነፃም ሆነ በግዢ የቧንቧ ውሃ የሚታደልበት ስፍራ፣ ቢርካም ይባላል።

ቦከቦከ ግ በሰበሰ። *ከእድሜው ብዛት የተነሳ የዛፉ ስር ቦከቦከ።*

ቡክቡካ ስ ጪሱ ጥሩ መአዛ ወይም ሽታ ያለው እንጨት፣ ሰራሰር።

ቦካ "ቦኬ"ን ተመ.

ቦኸ ግ 1. ኩፍ፣ ብድግ አለ፣ ለመጋገር ደረሰ (ሊጥ)። 2. ጨቀየ፣ ጭቃ ሆነ (መሬት)። 3. ለቤት ምርግ እንዲሆን ከጭድና ከውሃ ጋር የተረገጠ ወይም የታሸ ጭቃ ተብላላ፣ ሸተተ፣ ለምርግ ደረሰ። 4. በጣም ወፈረ፣ ሰባ። 5. ራደ፣ ፈራ። 6. ከመጠጠ፣ ሆመጠጠ።

ቡሃቃ(የቡሆ እቃ፥ ቦሃቃ) ስ 1. ሊጥ ወይም ቡኮ የሚዘጋጅበትና የሚቀመጥበት እቃ። 2. (ስድብ) የፊቱን ላይ ንፅህና የማይጠብቅ፣

ትርክርክ።

ቡሃቃ ለዩ አንድነት እየኖሩ በጋራ እያዘጋጁ ይመገቡ የነበሩ፥ ለየብቻ እያዘጋጁ ለየብቻ መመገብ ያዙ፥ ተለያዩ።

ቡኮ(ቡሆ፡ቡኪ፥ቡኬት) ስ ከእርሾ ጋር በውሃ የተለወሰ ዱቄት፣ ሊጥ።

ማቡኪያ ስ 1. ሊጥ የሚቦካበት እቃ (ቆሬያት፣ ገበቴ፣ ትልቅ ሳህን)። 2. ቡሃቃ።

ቦኬ(ቦካ) ስ ከከብት ሆድ ውስጥ የሚገኝ እንደጠጠር ያለ ቢጫ እንክብል፣ ሳዙና።

ቦክሰኛ "ቦቀሰ" ስር ተመ.

ቦክስ ዝ.ክ.

ቦዘ ግ 1. ፈዘዘ፥ ነሆለለ፣ ዘነጋ። 2. መልኩ ተቀየረ፥ ገረጣ፣ ነበዘ።

ቦዝ ቅ ልበ ቢስ፥ ዝንጉ።

ቦዝ አንቀፅ ስ (ሰዋ.) እንደ "በልቼ"፥ "በልተን"፣ "በልተህ"፥ "በልቶ"፥....ያለ፣ ብዙውን ጊዜ በማሰሪያ አንቀፅነት የማይገኝ አንቀፅ ወይም የግስ እርባታ ክፍል።

ቦዘነ ግ 1. ስራ ፈቶ ዋለ። 2. ስራ ተወ፥ ቸል አለ። 2. ስራ ፈተ፥ ቦዘኔ ሆነ።

ቦዘና ሽሮ ስ ስጋ ጣል ጣል የተደረገበት ወይም ስጋ በመጠኑ ያለበት የሽሮ ወጥ፣ ቦዘና ወጥ እየተባለም ይጠራል።

ቦዘኔ ስ ስራ የሌለው፣ ስራ ፈት፥ አውደልዳይ።

ቦዘን ስ ስራ መፍታት።

ቦዘንተኛ ቅ 1. ስራ ፈት። 2. ቸልተኛ፣ ዝንጉ።

አቦዘነ ግ አሰነፈ፥ ስራ አስፈታ።

***ቦዠርቦዠር**

ተንቦዠርቦዠር ግ 1. በመጠጥ ሞቅታ ሁለንተናው ተደሰተ፥ ተፍነከነከ። 2. ተንቀገረቀገረ፥ ግራ ተጋባ። 3.ፈራ፥ ተርበደበደ።

አንቦዠርቦዠር ግ 1. በመጠጥ ሞቅታ ሰውነቱን አስደሰተ፥ አፍነከነከ። 2. አንቀገረቀገረ፥ ግራ አጋባ። 3. አስፈራራ፥ አርበደበደ።

ቦጮ^{1} ስ ተቀቅሎ የሚበላ እንደ ስኳር ድንች ያለ ስር ያለው ሃረግማ የሆነ የተክል አይነት።

ቦጮ^{2} ስ አሳማ።

ቦይ^{1} ስ ለውሃ ወይም ለፍሳሽ መሄጃ እንዲያገለግል ጎድጎድ እንዲል ተደርጎ የተቆፈረ የፍሳሽ መስመር።

ቦይ^{2} ስ የሻይ ወይም የሆቴል ቤት ወንድ አስተናጋጅ።

ቦይና ስ ስኳር ድንች የሚመስል፥ ሻካራ የሆነ ስር ያለው፥ ቅጠሉ ረዘም ብሎ ሰፋ ሰፋ የሚል፥ ስሩ ተቀቅሎ የሚበላ የተክል አይነት።

ቦደሰ ግ በሰፊው ገመሰ፥ ጎመደ፥ ቦጨቀ (የአንድን ነገር አካል)።

ቡድስ ቅ በሰፊው የተገመሰ፥ የተቦጨቀ።

ተቦደሰ ግ በሰፊው ተገመሰ፥ ተጎመደ፥ ተቦጨቀ።

ቦደነ^{1} ግ 1. ቀኝ እጁን ወደውጪ አድርጎ፥ ጋቢውን ወይም ኩታውን በቀኝ ብብቱ ስር በማሳለፍ በግራ ትከሻው ላይ አጣፋ፥ አደገደገ። 2. ከሚሰነዘርበት የዱላ ወይም የድንጋይ ጥቃት ለመከላከል ወይም ለምክቶሽ ይረዳው ዘንድ ልብሱን እግራ እጁ ላይ ጠመጠመ፥ ደገለለ። 3.ጋረደ፣ መከተ።

***ቦደነ**^{2} ወገነ፣ ቡድን አበጀ፣ ያዘ።

ቡድን ስ 1.አንድን የተወሰነ ተግባር በቅንጅት የሚያከናውኑ ሰዎች የሚገኙበት አካል። 2. የተወሰነ ወገን፣ ክፍል፣ ምድብ።

የቡድን መሪ ስ የቡድን አለቃ፥ ሃላፊ፣ አስተባባሪ።

የቡድን አባት ስ በተለይ እንደገና ባሉ የባህል ጨዋታዎች ላይ እንደ አለቃ ሆኖ በመሰየም ለራሱ ቡድን የሚሆኑትን ተጫዋቾች የሚመርጥና አብሮ የሚጫወት ሰው።

ተቧደነ ግ 1.ከቡድን አባቶች ፊት ቀርቦ ለመመረጥ አንዱ ከሌላው ጋር ተጣመረ፥ ተኳደነ፥ ተቀናጀ።2. ቦደነ።

አቧደነ ግ አንዱን ከሌላው ጋር አጣመረ፥ አኳደነ፥ አቀናጀ።

ቦዳ መሬት ስ የሰባ መሬት።

***ቦገቦገ**

ቦግታ ስ ብልጭታ፥ ተግታ (የመብረቅ፥ የብርሃን)።

ቦግ አለ ግ 1. ብልጭ፣ ተግ አለ፤ በራ። 2. ድንገት በሃይል ነደደ፥ ተቀጣጠለ (እሳት)። 3. ፏ ብሎ፥ ደምቆ ወይም ጎልቶ ታየ።

ቦግ ቦግ አለ ግ ብልጭ ብልጭ፥ ተግ ተግ አለ።

ተንቦገቦገ ግ 1. ተብለጨለጨ። 2. በሃይል ነደደ፣ ተንበለበለ።

አንቦገቦገ ግ 1. አብለጨለጨ፥ አንተገተገ። 2. አንቀለቀለ፣ አንበለበለ።

***ቦጠለቀ**

ቡጥልቅ አለ ግ ተቦጠለቀ።

ተቦጠለቀ ግ ድንገት በሃይል ተስፈንጥሮ ወጣ (ትውከት፥ አክታ፥...)።

ቦጠቦጠ ግ 1. ቦረቦረ፥ የውስጥ የዕሶስጡን ወይም ልብ ልቡን በላ (ለምሳሌ የዱባን)። 2. በጥርሱ እየፈለቀቀ በላ (የባቄላ፥ የአተር

እሸትን)፡፡3. ጎጠጎጠ፥ ኮረኮረ (ብብትን)፡፡ 4. በቡጢ ውስጥ ውስጡን መታ፥ ደበደበ፡፡ 5. (ዘይ.) ውስጥ ውስጡን በላ፤ በዘበዘ፥ አራቆተ (ገንዘብን)፡፡

ቡጢ ስ የተጨበጠ እጅ፥ ጡጫ፡፡

ቡጥ ስ 1. የዳቦ ውስጠኛ ክፍል፥ ልብ፡፡ 2. የእንጨት መሃለኛውና ለስላሳው ክፍል፥ ልቡ፡፡ 3. ጉጥ፡፡ 4. የባቄላና የአተር እሸት ፍሬ ልባስ፡፡

***ቦጨረቀ**

ቦጭራቃ ቅ 1.ቦጭቧጫ፡ ውሃ የበዛበት (ወጥ፡ ጠላ፡...)፡፡ 2. (ዘይ.) ቁምነገር የሌለው፡ ፍሬቢስ፡፡

ተንቦጫረቀ (ተምቦጫረቀ) ግ 1. እጁን ወይም እግሩን ውሃ ውስጥ ከቶ ተንቧቸ፡ ተፈራገጠ ወይም በሙሉ አካሉ ውሃ ውስጥ ገብቶ ተወራጨ፡ ተንደፋደፈ፡፡ 2. ሙሉ፥ መልክ ሳይዝ ቀረ፡ ተበላሸ፡፡

አንቦጫረቀ(አምቦጫረቀ) ግ1. አንቧቸ፡ በጠበጠ (ውሃን)፡፡ 2 መልክ፡ ቅጥ አሳጣ፡ አበላሸ፡፡

ቦጨቀ ግ 1. ቦተረፈ፡ ቦደሰ፥ ቀደደ፡ ነጨ፡ ዘነጠሰ፡፡ 2. ጥጥን አፍታታ፡ አባዘተ፡፡3. (ዘይ.) አማ፥ በሃሜት የሰው ስም አነሳ፡፡

ቡጫቂ ቅ ከዋናው አካሉ ላይ በመቦትረፍ ወይም በመቀደድ ተለይቶ የወጣ (ቁራጭ፥ ዝንጣይ፥ ቅዳጅ፡...)፡፡

ቡጭቅ ቅ 1.ቡጫቂ፡፡ ስ 2. የተባዘተ ጥጥ፡ ባዘቶ፡፡

ቡጭቅጫቂ ቅ የተበጣጠሰ፥ የተቀዳደደ፡፡

ተቦጨቀ ግ ተቦተረፈ፥ ተቀደደ፡፡

ተቦጫጨቀ ግ ተበጣጠሰ፡ ተቀዳደደ፡፡

ተቧጨቀ ግ 1. እርስ በርስ ተናከሰ፡ ተባላ፡፡ 2. ተቀራመተ፥ ተሻማ፥ ተናጠቀ፡፡

***ቦጨቦጨ**

ቦጭቧጫ ቅ 1. ውሃ የበዛበት፥ ጣእም የሌለው፡ መናኛ የሆነ (ጠላ፡ ወዘተ ...)፡፡ 2. በቅቧቃ፡ ቡከን፥ ፈሪ፡፡ 3. (ዘይ.) ቁምነገር የሌለው፥ ፍሬቢስ የሆነ ነገር፡፡

ቡጭ ቡጭ አለ ግ 1.ጎደል ያለ ፈሳሽ ነገር (ለምሳሌ ውሃ) የያዘ እቃ ሲነቀነቅ በውስጡ ያለው ፈሳሽ የሚያሰማውን አይነት ድምፅ አሰማ፡፡ 2. (ዘይ.) ከሃዘን፡ ከርህራሄ የተነሳ ተንሰፈሰፈ (ሆድ)፡፡

ተንቦጫቦጨ(ተምቦጫቦጨ) ግ 1. ቦጭ ቦጭ የሚል ድምፅ አሰማ፡፡2. ፍርሃት ፍርሃት አለው፡፡ *ከዘመድ ሲለይ ሆዱ ተንቦጫቦጨ፡፡*

አንቦጫቦጨ(አምቦጫቦጨ) ግ 1.ወዘወዘ፡ ናጠ፥ ቦጭ ቦጭ የሚል ድምፅ እንዲሰጥ አደረገ (ጎደሎ ፈሳሽ የያዘን እቃ)፡፡ 2. (ዘይ.) አበላሸሸ፡ ጣእም አሳጣ፡፡

እንቡጭቡጭ ቅ 1. ጣእመቢስ፥ መናኛ፡ የማይረባ፡፡ 2. ቡከን፥ ፈሪ፡፡

ቦጭራቃ "*ቦጨረቀ" ስር ተመ.

ቦጭቧጫ "*ቦጨቦጨ" ስር ተመ.

ቦፍ

ቦፌ ቅ ውፍረት እንጂ ጥንካሬ የሌለው፡ ውስጠ ልል፡፡

ቦፍ አለ ግ ዘጭ አለ፡ በአወዳደቁ ቦፍ የሚል አይነት ድምፅ አሰማ፥ ወደቀ፡፡

እምቦፍ(እንቦፍ) አለ ዝ.ከ.

ቧ የ **"በ"** ፊደል ፍንፅቅ ዘር፡፡

ቧሄ ሃረግ ስ ግንዱ ነጭ የሆነ ሃረግ፤ ሃረግሬሳ፥ እበሳቢቅ እየተባለም ይጠራል፡፡

ቧሄ ቁራ ስ ራሱ ላይ ነጭ ምልክት ያለበት ቁራ፡፡

***ቧለተ**

ቧልት(ቧልታ) ስ 1. ፌዝ፡ ቀልድ፥ ዋዛ ፈዛዛ፡፡ 2. ተረብ፡፡

ቧልተኛ ቅ 1.ፌዘኛ፡ ቀልደኛ፡፡ 2. ተረበኛ፡፡

አቧለተ ግ 1. አፌዘ፤ ቀለደ፡፡ 2. ተረበ፡፡

ቧምቧ "ቧንቧ"ን ተመ.

***ቧቧ**

ተንቧቧ(ተምቧቧ) ግ በብዛት ፈሰሰ፥ ተንዶለዶለ(ፈሳሽ)፡፡

አንቧቧ (አምቧቧ) ግ በብዛት አፈሰሰ፥ አንዶለዶለ(ፈሳሽን)፡፡

***ቧተረ**

አንቧተረ(አምቧተረ) ግ ያዙኝ ልቀቁኝ በማለት ተጋበዘ፥ የተነሳሁበትን አደርጋለሁ፥ አትገላግሉኝ ብሎ ወዲያ ወዲህ ዘለለ፤ ተቅነበነበ፥ ጉራ ነዛ፡ ሳያደርገው ተግደረደረ፡፡

አንቧታሪ (አምቧታሪ) ቅ ጉረኛ፥ የማያደርገውን እንደሚያደርግ አስመስሎ የሚታይ፥ ለመደባደብ የሚቃጣ፥ ለማስፈራራት የሚሞክር፡፡

***ቧቸ**

ተንቧቸ(ተምቧቸ) ግ 1. በውሃ ተንቦጫረቀ፡፡ 2. ተጫወተ፡ ተንጫጫ፥ ተንቻቻ፡፡ 3. እንደልቡ፥ እንደፈለገው ሆነ፡፡ *ያባትህን ቤት ማን ይከለክልሃል ግባና ተንቧቸበት፡፡*

አንቧቸ(አምቧቸ) ግ 1. ውሃ አንቦጫረቀ፡፡ 2. አጫወተ፡ አንጫጫ፥ አንቻቻ፡፡

ቧንቧ(ቧምቧ) ስ ውሃ ወይም ፈሳሽ ነገር በውስጡ ሊሄድበት የሚችል፡ ክብነት ያለው

ውስጠ ክፍት ብረት ወይም ፕላስቲክ ወይም ሌላ ነገር።

ቧገተ(ባጎተ) ግ 1. በየውድማው እየዞረ እህል ተመፀወተ። 2. ለመነ፤ ቀፈፈ።

ቧጋታ(ባጎታ) ስ 1. በየውድማው እየሄዱ እህል የመመፅወት፤ የመቀበል ድርጊት። 2. ልመና፤ ቀፈፋ።

ቧጋች ስ 1. የውድማ ላይ ተመፅዋች። 2. ለማኝ።

አቧገተ ግ 1.ውድማ ላይ ለተገኙት ተመፅዋቾች ከምርቱ እየፈሰ ሰጠ፤ መፀወተ። 2. አለመነ፤ ቸረ፤ ሰጠ።

አቧጋች ቅ 1.ውድማው ላይ ከተንባለለው ምርት ወይም ከተቆለለው እህል ለተመፅዋቾች እየፈሰ የሚሰጥ። 2. አስማኝ፤ የሚቸር።

ቧጠጠ ግ 1. በጥፍር ሟጨረ፤ ቧጨረ፤ ጫረ። 2. ፍግፍግ አድርጎ ጠረገ፤ ፈቅፍቆ አነሳ(እንደ ጭቃ፤ አዛባ፤ ቅቤ፤...ያሉን ነገር ከሚገኝበት ቦታ ላይ)። 3. ጠረገ(ጉረሮን)። 4. በእጁ ጣቶች ወግቶ ያዘ፤ አጥብቆ ጨመደደ። *ዳገቱን የወጣው በእጁ እየቧጠጠ ነው።*

ቡጥጫ ስ መቆፈሪያ፤ በጥፍር መቧጠጥ።

ቧጨረ ግ ሟጨረ፤ ጫረ።

ቡጭር ቅ የተሟጨረ፤ የተጫረ።

ቡጭርጭር ቅ 1. አካሉ በጥፍር ወይም በሌላ ነገር የተሞጫጨረ፤ የተቧጠጠ። 2. ትክክለኛውን ቅርፅ ያልያዘ፤ የተወላገደ (ፅሁፍ)።

ተቧጨረ ግ ተሟጨረ፤ ተጫረ።

ቨ

ቨ በዚህ መዝገበ ቃላት ፊደል ተራ መሰረት ከ"በ" ቀጥሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል (ግእዙ ሆሄ)።

ቩ የ"ቨ" ፊደል ካእብ ዘር።

ቪ የ"ቨ" ፊደል ሳልስ ዘር።

ቪላ [ቢ.ት] ስ ፎቅ ያልሆንና የተለያዩ ክፍሎች ያሉት፣ ለብቻው ራሱን ችሎ በዘመናዊ መልክ የተሰራ መኖሪያ ቤት።

ቪታሚን(ቫይታሚን) ስ ለሰውም ሆነ ለእንስሳት ጤንነት አስፈላጊ የሆነ፥ ከተለያዩ ምግቦች ሊገኝ የሚችል ንጥረ ነገር።

ቪኖ(ቢኖ) ስ ከወይን የሚዘጋጅ የአልኮል መጠጥ፣ ወይን ጠጅ።

ቪዛ ስ አንድ ሰው ወደ አንድ ሌላ አገር እንዲገባ፣ እንዲተላለፍ ወይም ከአገር ውስጥ እንዲወጣ መፈቀዱን ለመግለፅ በሚመለከተው አገር ባለስልጣን በተጓዡ ፓስፖርት ላይ የሚደረግ ማህተም።

ቪዛ ተሰጠው/አገኘ/ተመታለት ወደ አንድ አገር እንዲገባ ወይም ከአገር እንዲወጣ ፈቃድ አገኘ።

ቪዛ ታደሰለት በአንድ ሌላ አገር ውስጥ እንዲቆይ የተፈቀደለት ጊዜ ወይም ከአገር ውስጥ እንዲወጣ የተሰጠው የጊዜ ገደብ ተራዘመለት።

ቪዮላ ስ ከቫዮሊን ከፍ የሚል የክር ሙዚቃ መሳሪያ (ስእሉን የሙዚቃ መሳሪያ ስር ተመ.)።

ቪዲዮ ስ በቪዲዮ ክር (ጥብጣብ) ላይ የተቀረፀን ምስልና ድምፅ በቴሌቪዥን አማካይነት ለማሳየትና ለማሰማት የሚያስችል መሳሪያ።

የቪዲዮ መቅረጫ ስ በቪዲዮ ክር ላይ ምስልና ድምፅን ለመቅረፅ የሚያስችል መሳሪያ።

የቪዲዮ ክር ስ በቴሌቪዥን ሊተላለፍ የሚችል ምስልና ድምፅ የሚቀረፅበት ማግኔታዊ ጥብጣብ።

ቫ የ"ቨ" ፊደል ራብእ ዘር።

ቫርኒሽ ስ በአብዛኛው እንደ ጠረጴዛ፣ ሳጥን፣ መደርደሪያ በመሳሰሉ ወይም ሌሎች የእንጨት ስራዎች ላይ ከላይ በስሱ እንዲያለብስ ተደርጎ የሚቀባና መልክ የሚሰጥ፣ እንደ ቀለም ያለ ፈሳሽ ነገር።

ቫክዩም ስ ከማንኛውም አይነት ነገር ወይም ጋዝ ነፃ የሆነ ባዶ ቦታ ወይም በአንድ ሳጥን ወይም በሌላ መያዣ ነገር ውስጥ የሚገኝ አየር በሙሉ ወይም በከፊል ከውስጡ የወጣለት ባዶ ቦታ።

ቫውቸር ስ ለአንድ ነገር ክፍያ መፈፀሙን የሚያሳይ ሰነድ፥ ደረሰኝ።

ቫዝሊን ስ ለሰውነት ቆዳ ማለስለሻና ማውዣ የሚያገለግል የቅባት አይነት።

ቫይረስ ስ ከባክቴሪያ የሚያንስ፥ ተላላፊ በሽታን የሚያስከትል ህዋስ።

ቫይታሚን "ቪታሚን"ን ተመ.

ቫዮሊን ስ አገጭ ስርና ትከሻ ላይ አድርገው ዱላን በመሰለ ማንዘሪያ እንደመሰንቆ እየገዘገዙ የሚጫወቱበት የክር ሙዚቃ መሳሪያ (ስእሉን የሙዚቃ መሳሪያ ስር ተመ)።

ቬ የ"ቨ" ፊደል ሃምስ ዘር።

ቬሎ ስ ሴት ሙሽራ የጋብቻ ስነስርአቷን በምትፈፅምበት እለት የምትለብሰው በገበር ተደርጎ በልዩ ሁኔታ የሚሰፋ ስስ የሆነ የሰርግ ልብስ።

ቬሎ

ቬቶ ስ ድምፅን በድምፅ ወይም ውሳኔን በውሳኔ የመሻር ስልጣን።

ቬነስ(ቬኑስ) ስ በሜርኩሪና በመሬት መካከል የምትገኝ ከፀሃይ ሁለተኛ ተራ ላይ ያለች ፕላኔት። በተጨማሪ **"ፕላኔት"**ን ተመ.

ቭ የ"ቨ" ፊደል ሳድስ ዘር።

ቮ የ"ቨ" ፊደል ሳብእ ዘር።

ቮልት ስ የኤሌክትሪክ ሃይል መጠን መለኪያ አሃድ።

ቯ የ"ቨ" ፊደል ፍንፅቅ ዘር።

ቯልስ ስ በለስላሳ ሙዚቃ እየታጀቡ ጥንድ በመሆን በዝግታ የሚደነሱት ዳንስ።

ተ

ተ በዚህ መዝገበ ቃላት ፊደል ተራ መሰረት ከ "ቨ" ፊደል ዘር ቀጥሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል (ግእዙ ሆሄ)።

ተ (ሰዋ.) 1. በአድራጊ አምድ ግስ መነሻ ላይ እየተቀጠለ ተደራጊ አምድን የሚመሰርት ምእላድ። *ገደለ→ተገደለ*፡ 2.ድርጊት ተቀባይነትን የሚያሳይ ምእላድ። *ተሾመ*፡ 3. በአደራራጊ አምድ ግሶች መነሻ ላይ እየተቀጠለ ሁለት ነገሮች እርስ በርስ አንድ ነገር መደራረጋቸውን ለመግለፅ የሚያገለግል፥ ተደራራጊ አምድን ለመመስረት የሚያስችል ምእላድ። *ፈላለገ→ተፈላለገ*፡ 4. በአስር አምድ ላይ እየተቀጠለ ተዳራጊ አምድን የሚመሰርት ምእላድ። *ጋደለ→ተጋደለ*፡ 5. በአንድ አይነት ሁኔታ ውስጥ መገኘትን ለማመልከት የሚያገለግል ምእላድ። *ተቸገረ / ተደሰተ*።

ተሃዋስያን (ነ.ቁ.**ተሃዋሲ**) ስ ጥቃቅን የሆኑ ተንቀሳቃሽ ነፍሳት በሙሉ።

ተለለ^{1} ግ ፈሰሰ፡ ኮለል ብሎ ወረደ።

ተለል አለ ግ ኮለል ብሎ ወረደ። *እንባው በጉንጮቹ ላይ ተለል ብሎ ወረደ።*

ተለለ^{2} ግ ጠራ፥ ጠለለ፥ ጥሩ ሆነ (ፈሳሽ)።

አተለለ ግ አጠለለ፥ አጠራ።

ተለሳ ስ መስመር፡ መደዳ፥ ረድፍ።

ተለመ ግ 1. አንድ ፈር አወጣ፥ ቀደደ፥ ሰነጠቀ፥ ነመሰ (በማረሻ)። 2. አቀደ፥ ወጠነ፡ ጀመረ። 3. ሰንበር እስኪያወጣ በጅራፍ፡ በአርጩሜ ገረፈ።

ትልም ስ 1. አንድ ጊዜ የተሄደበት የእርሻ ፈር፥ ጅምር። 2. እቅድ፥ ጅምር፡ ውጥን። 3. በግርፊያ ምክንያት ሰውነት ላይ የወጣ ሰንበር፡ ምልክት።

ተተለመ ግ 1. ትልም ወጣ። 2. ተጀመረ፥ ተወጠነ።

ተለምዶ "ለመደ"ስር ተመ.

ተለቀ ግ 1. አደገ፥ ትልቅ ሆነ። 2. ከሚፈለገው መጠን በላይ ሆነ።

ታላቅ ቅ 1. (ብ.ቁ.**ታላላቅ**) ከፍ ያለ (በእድሜ፥ በማእረግ)። 2. የስጋ ብልት ስም።

ትልቅ(ብ.ቁ. **ትልልቅ፥ትላልቅ**) ቅ 1. ታላቅ፤ በቁመት፥ በርዝመት፥ በመጠን፥በእድሜ፥ በማእረግ ከፍ ያለ። 2. ጥሩ፤ ከፍተኛ የሆነ። *ትልቅ ስራ ሰርቷል።*

አተለቀ ግ ትልቅ አደረገ ፥ አገዘፈ።

ተለተለ ግ 1. ተረተረ፥ ፈታ፥ መዘዘ፥ ለየ (ማግን ከድር)። 2. ቀደደ፥ ሰነጠቀ። 3. በጣ፤ ሸነተፈ (ሰውነትን በስለት)። 4. ገረፈ፥ አሰነበረ፥ አደማ (ሰውነትን በጅራፍ፥ በአለንጋ፥...)።

ትልታይ ስ 1. ከድር የወጣ ማግ ወይም ከማግ የተለየ ድር። 2. ቀጠን ረዘም ያለ የጨርቅ ቅዳጅ።

ትልትል ቅ 1. ትርትር(ጨርቅ)። 2. ስንጥቅ፥ ብጥ፥ ስንትር (ሰውነት)።

ትልትላት ስ ከሰውነት ላይ በስለት የተደረገ ትፍትፋት፥ ስንጥቃት፥ ስንትራት።

ተለዘ ግ ደከመ፥ አቅም አጣ።

ትልዝ.ትልዝ አለ ግ ደከመ፥ ጭልጭል አለ።

ተሳ ግ በመበስበስ ወይም በመበላሸት ትል አወጣ፥ ፈጠረ።

ትል ስ አካሉ በለሰላሳ ቆዳ የተሸፈነና በበሰበሱ ነገሮች ላይ፥ በውሃና በአፈር ውስጥ የሚገኝ፥ በደረት እየተሳበ የሚሄድ፥ መተጣጠፍና መጠቅለል የሚችል አነስተኛ ነፍሳት።

ትሳበራ(ትልአበራ) ስ በጨለማ ውስጥ ስትሄድ ብልጭ ድርግም የሚል ብርሃን የምታሳይ ትል።

ትሳም ቅ 1. ትል ያለበት ወይም የበዛበት። 2. (ነውር፥ ስድብ) የበሰበሰ፥ ቆሻሻ።

አተሳ ግ 1. ትል አወጣ። 2. እንዲተሳ አደረገ።

ተሳሳ "*ታሰለ" ስር ተመ.

ተልባ ስ 1. ፍሬው ቅባትነት ያለው የሰብል አይነት። 2. ከተልባ ፍሬ በዱቄት መልክ ተዘጋጅቶ በዘይት ፈንታ ውጥ ውስጥ የሚገባ ማጣፈጫ። 3. (ዘይ.) በቃሉ የማይረጋ፥ የማይታመን፥ ሸርታታ፤ "የተልባ ስፍር"ም ይባላል።

ተልባ ማሻ ስ ተልባ የሚታሸበት ገበቴ።

[የ] ተልባ ድርጥ ስ በውሃ የታሸ የተልባ ልጥልጥ።

ተልብማ ቅ መልኩ ተልባ የሚመስል።

ተልእኮ ስ አንድን ነገር ለማከናወንና ከግብ ለማድረስ የያዙት አላማ፤ የሚቀበሉት ሃላፊነት ወይም ግዳጅ። *ሀገርንና ወገንን ማገልገል የዜጎች ሁሉ ተልእኮ ሊሆን ይገባል።*

የተልእኮ ትምህርት ስ በተወሰነ የትምህርት ዘርፍ ላይ የተዘጋጁ ፅሁፎችን ከትምህርት ሰጭው ክፍል ጋር በመላላክ የሚካሄድ ትምህርት፤ የመላላክ ትምህርት።

ተልካሻ(ተልካሳ) ቅ 1.ደካማ፥ አቅመቢስ። 2. ጎታታ፥ ሰነፍ፥ ስራ ጠብ የማይልለት። 3.

መናኛ፥ ተራ፥ የማይረባ።

ተመመ ግ 1. እም... የሚል ድምፅ አሰማ (የውሃ አወራረድ፥ የብዙ ሰው ንግግር፥ የንብ ጉዞ፥...)። 2. ብዙ ሆኖ ተጓዘ። 3. ድምፅ አሰማ፥ ጮሀ (ከበሮ፥ አታሞ)።

ተመሰጠ "መሰጠ"ስር ተመ.

ተመተመ ግ 1. መታ፥ ለተመ፥ ገጨ። 2. አስተካከለ፥ ደመደመ። 3. እንጀራ ወይም ዳቦን በማብያው ጠቀሰ፥ አረመደ። 4. በማባበል በእጁ ቸብ ቸብ፥ ነካ ነካ አደረገ (ህፃንን፥ ፈረስን፥...)።

ትምትም ስ በልጥፍና በልስን መካከል ያለ የቤት ምርግ ስራ አይነት።

ተመነ ግ ገመተ፥ ወሰነ(ዋጋን)።

ተመን ስ ዋጋ የዋጋ ግምት።

ተመን አወጣ የዋጋ ዝርዝር፥ ግምት አወጣ፥ ዋጋ መደበ።

ተማኝ ስ ዋጋ መዳቢ።

ተመከሮ "መከረ" ስር ተመ.

ተሙን(ትሙን) ስ የብር አንድ ስምንተኛ የነበረ የጥንት ዘመን ገንዘብ።

ተማሪ ""መሃረ" ስር ተመ.

ተማኝ "ተመነ" ስር ተመ.

ተምር(ቴምር) ስ በጣም ሞቃት የሆነ የአየር ጠባይ ባለው አካባቢ የሚበቅል፥ ዘንባባ የሚመስል ረዣዥም ቅጠሎች ያሉትና ሲበስል ቡና አይነት መልክ የሚኖረው፥ ውስጡ ቀጭንና ሞላላ የሆነ ጠንካራ የዘር ፍሬ ያለው ጣፋጭ ፍሬ የሚያፈራ ተክል፤ ፍሬውም ተምር ይባላል።

ተምሳሌት "መሰለ" ስር ተመ.

ተምች ስ የእህል ቡቃያን ወይም ሳርን በልቶ የሚያጠፋ የትል አይነት።

ተሞከሮ "ሞከረ" ስር ተመ.

ተረር^1 ስ ፍሬው የሚበላ አነስተኛ የእፅዋት አይነት።

ተረር^2

ተረር አለ ግ ሰንጥቅ አለ፥ ተቀደደ፥ ተተረተረ።

ተረር ብሎ ሄደ በአንድ መስመር ተከታትሎ ሄደ።

ተረር አደረገ ግ ሰንጥቅ፥ ክፍል አደረገ።

ተረበ ግ 1. ቀለደ፥ አፌዘ፥ አላገጠ፥ አሾፈ። 2. ነደፈ፥ ጠቅ አደረገ፥ ወጋ(በነገር)።

ተረብ ስ ቀልድ፥ ፌዝ፥ ሽሙጥ።

ተረበኛ ቅ ቀልደኛ፥ ፌዘኛ፥ ጨዋታ አዋቂ።

ተራቢ ቅ አሽሟጣጭ፥ ፎታች።

ትረባ ስ ማሽሟጠጥ፥ ፋተታ።

ተረተ ግ 1. በእውነት ያልተፈፀመን ነገር ወይም የፈጠራ ታሪክን፥ በእውን እንደተደረገ አድርጎ ተናገረ፥ አወራ፥ ተረከ። 2. ምሳሌያዊ ንግግርን በንግግሩ ውስጥ ተጠቀመ።

መተረቻ ስ መዘባበቻ፥ መቀለጃ ወይም ለመቀለጃ በምሳሌነት የሚጠቀስ፥ የሚቀርብ ድርጊት።

ተረት ስ 1. እውነት ለመሆኑ ማስረጃ የሌለው ወይም እንደተደረገ ሆኖ የሚነገር በፈጠራ የተቀነባበረ ታሪክ። 2. ምሳሌያዊ አነጋገር፤ አባባል።

ተረት ተረት በተለይ ረዥም ተረት የሚያወራ ሰው ለተረቱ እንደ መግቢያ ወይም እንደመነሻ አድርጎ የአድማጮቹን ትኩረት የሚጠይቅበት ቃል (አድማጩ "የላምበረት" ወይም "የመሰረት" በማለት ተረቱን ለማዳመጥ መዘጋጀቱን ይገልፃል)።

ተረትና ምሳሌ ምሳሌያዊ አነጋገር።

የተረት አባት ስ ልጆችን ሰብስቦ ተረት የሚያወራ ተረት አዋቂ ሽማግሌ።

ተረተኛ ቅ 1. ተረት አዋቂ፥ ባለተረት። 2. በሆነ ባልሆነው ተረት ማቅረብ የሚወድ።

ተራች ስ ተረት ተናጋሪ።

ተተረተ ግ በተረት መልክ ተነገረ።

ተረተረ ግ 1.ፈታ፥ ለያየ፥ አላቀቀ (የተሰፋን፥ የተገመደን፥ የተቋጠረን ነገር)። 2. ቀደደ፥ ሰነጠቀ። 3. ፈነከተ፥ ከፈለ፥ ገመሰ። *ላፍቷን በቁላ ተረተረው*። 4. አረሰ፥ ገመሰ። 5. ውሸት ተናገረ፥ አወራ።

ትርትር ቅ ሰንጥቅ።

ትርታሮ ስ ገመስ፥ ገመስ የሚያደርጉት የአስተራረስ አይነት፤ ጭፍለቃ፤ ገመሳ።

ተተረተረ ግ 1. እንደገና ተፈታ፥ ተለያየ፥ ተላቀቀ (የተገመደ፥ የተሰፋ ነገር)። 2. ተቀደደ፥ ተሰነጠቀ። 3. ተፈነከተ፥ ተከፈለ፥ ተገመሰ። 4.ታረሰ፥ ተገመሰ። 5.(ዘይ.) ዋሸ።

*ተረተረ

ተረተር ስ የተራራ፥ የኮረብታ፥ የጉብታ ተዳፋት።

አተረተረ ግ በረድፍ፥ በተራ ተሰለፈ፥ ተሰደረ።

ተረተኛ "ተረተ" ስር ተመ.

ተረት ዝ.ከ.

ተረኛ "ተራ" ስር ተመ.

ተረከ ግ ስላለፈ ነገር ዝርዝር ተናገረ፥ አወራ፥ አወጋ፥ አተተ።

ተራኪ ስ ታሪክ ተናጋሪ፤ ፀሃፊ፤ አንባቢ።

ታሪክ ስ 1. በጊዜ ቅደም ተከተል የሚሄድ፥ ስላለፈ የህዝብ፥ የመንግስታት፥ የመሪዎች ድርጊትና ሁኔታ የሚዘረዝር፥ የሚያጠናና አጠቃላይ መግለጫ የሚሰጥ የህብረተሰብ ሳይንስ። 2. የአንድን ነገር ሁኔታና የእድገት ሂደት የሚያሳይ ዝርዝር መግለጫ። *የአማርኛ ስነፅሁፍ ታሪክ*። 3. በልቦለድ ፈጠራ ላይ የተመሰረተ የአንድ ወይም የብዙ ሰዎች የተያያዘና የተጠላለፈ ክንዋኔን፡ የኑሮ ገጠመኝ ሂደትን የሚገልፅ ፅሁፍ።

ታሪክ ነው ግሩም፥ አስደናቂ ነው።

ባለታሪክ ስ 1. የአንድ አኩሪ ስራ ክንዋኔ ባለቤት የሆነ፥ ጥሩ ወይም ትልቅ ስራ የሰራ። 2.ገፀ ባህርይ።

ታሪክ ፀሃፊ የህዝብን፡ የመንግስታትን፡ የመሪዎችን ክንዋኔ እያጠና መዝግቦ አጠቃላይ ገፅታውን የሚያሳይ ባለሙያ፥ ፀሃፊ ታሪክ።

ታሪከኛ ቅ 1. ተደናቂ፥ አስገራሚ። 2. ዝነኛ፡ ስመጥር።

ታሪካዊ ቅ 1. በታሪክ የተመዘገበ ክንዋኔ የተከሄደበት፥ በታሪክ የሚታወቅ። *ታሪካዊ ስፍራዎች /ታሪካዊ ቅርሶች*፡ 2. የተለየ ወይም ድንቅ የሆነ ነገር ወይም ድርጊት የተፈፀመበት። *በዚህ ታሪካዊ ቀን...*።

ትረካ ስ ታሪክ መተረክ።

ተረከከ ግ ሰነጠቀ፡ ፈነከተ።

ተንተረከከ ግ 1. በሰለ፥ ጎመራ (ፍራፍሬ)። 2. ፍም ወረደ፥ መረተ (የእሳት)። 3. ወፈረ ደለበ።

አንተረከከ ግ 1. አበሰለ(ፍራፍሬን)። 2. ፍም እንዲወርደው አደረገ (እሳትን)። 3. አወፈረ፥ አደለበ፥ አሰባ።

ተረከዝ ስ ከሂላ በኩል የሚታየውና መሬት የሚረግጠው የውስጥ እግር ክፍል(ስእሉን በሁነት ስር ተመ.)።

ባለተረከዝ ጫማ በተረከዙ በኩል መርገጫው ረዥም የሆነ ጫማ፥ ታኮ ጫማ።

ተረከዘ ሎሚ ስንጥቅ ወይም ምልክት የሌለበት እንደሎሚ የሚያምር ተረከዝ ያላት።

ተረከዘ ክት ቅርፀ መልካም የሆነ አጭር ተረከዝ ያላት።

ተረከሰ ግበሚነድ ወይም በሚቃጠል የእንጨት፡ የጧፍ፥... ጫፍ ላይ የሚገኘውን ክሳይ ወይም አመድ አስወገደ።

መተርከሻ ስ ከእንጨት ወይም ከሸክላ... የሚሰራ የሲጋራ አመድና ቁራጭ ማጠራቀሚያ።

ትርኳሽ ስ እሳቱ፥ ፍሙ እንዲጠፋ የተደረገ (እንጨት፥ ሲጋራ፥...)።

ተረገረገ ግ ተጠቀጠቀ፡ ታጨቀ፥ ሞላ።

ተረጎመ ግ 1. በአንድ ቋንቋ የተነገረን ሃሳብ ወደ ሌላ ቋንቋ መለሰ፡ ለወጠ። 2. አንድን አባባል ወይም የተነገረ ነገር ፈታ፡ አብራራ። 3. አንድም እንደዚህ እንደዚህ ማለት ነው፥... እያለ በቅዱሳት መፃህፍት ውስጥ የሚገኝን አንድ ሃሳብ ወይም አባባል በተለያየ መልክ እያገናዘበ ዘርዝሮ፡ አፍታትቶ፥ ተንትኖ አስረዳ። 4. አንድን ሃሳብ በአንድ በሌላ አይነት መልክ ተረዳ።

ተርጓሚ ስ 1. በአንድ ቋንቋ የተነገረን ሃሳብ በሌላ ቋንቋ ለውጦ የሚናገር፡ የሚያሰማ፥ "አስተርጓሚ"፥ "ትርጁማን"ም ይባላል። 2. በአንድ ቋንቋ የተፃፈን ነገር ወደሌላ ቋንቋ እየመለሰ የሚፅፍ። 3. ቅዱሳት መፃህፍትን በአንድምታ ትርጓሜ መንገድ የሚተነትን።

ተርጓሚ ደርጋሚ በፅሁፍ ተፅፎ እንዲተላለፍ የሚፈለገውን መልእክት ሌላ ፍቺ በመስጠት አዛብቶ ወይም አጣሞ የሚያቀርብ።

ትርጉም ስ 1. ከአንድ ቋንቋ ወደ ሌላ ቋንቋ የተመለሰ፡ የተለወጠ፡ የተተረጎመ ሃሳብ፥ ፅሁፍ፥...። 2. የአንድ ቃል ፍቺ። 3. አንድ የተባለን፥ የተነገረን፥ የተፃፈን፥... ሃሳብ ለማብራራት ወይም ግልፅ ለማድረግ የተነገረ ወይም የተሰጠ ተጨማሪ መግለጫ።

ትርጉም ሰጠው በሌላ ሃሳብ (መልክ) ተረጎመው፡ በመጥፎ ተረዳው።

ትርጉም አይሰጠኝም ስሜት አይሰጠኝም፡ አያረካኝም አያስደስተኝም።

ትርጉም የለውም ምንም የሚያመጣው ለውጥ የለም፥ ጥቅም የለውም። *ባለፈ ነገር ፀፀት ማብዛት ትርጉም የለውም*።

ትርጓሜ ስ 1.ፍቺ፥ ማብራሪያ። 2. አንድ ሃሳብ ተስፋፍቶ፥ ተዘርዝሮና ተመስጥሮ በአንድምታ የአተረጓጎም ወይም የአፈታት ስልት የሚቀርብበት የትረካ፡ የገለፃ፥ የትንተና መንገድ።

ተተረጎመ ግ 1. ተፈታ፥ ተብራራ፥ ተገለፀ። 2. በአንድ ቋንቋ የተነገረ ቃል፡ አረፍተነገር፡...ወደሌላ ቋንቋ ተመለሰ፥ ተለወጠ። 3. አንድ አባባል ወይም አገላለፅ ተናጋሪው ያላሰበውን ትርጉም ወይም መልእክት አስተላለፈ።

አስተረጎመ ግ በአንድ ቋንቋ የተነገረውን ወደ ሌላ ቋንቋ በቃል እየተረጎመ ተናገረ።

አስተርጓሚ የ "**ተርጓሚ**"ን 1ኛ ፍቺ ተመ.

ተረፈ ግ 1. ከሚፈለገው መጠን በላይ ሆነ፥ ከተወሰነው መጠን አለፈ፡ በዛ (በቁጥር፡ በስፍር፥...)። 2. ቀረ (ሳያልቅ፥ ሳይጠፋ፥...)። *አንድ ብር ተረፈኝ*፡ 3. ለሌላ ሆነ፥ ወደ ሌላ

ተሻገረ። *ለሃጥኣን የወረደ ለፃድቃን ይተርፋል።* 4. ሞላ። *ሃብት ተረፈው።* 5. አገኘ። *በጠጪነቱ የተነሳ በሽታ ተረፈው።* 6. ዳነ፡ አመለጠ (ከበሽታ፥ ከሞት፥...)።

አልተረፈም በጣም ተጎድቷል።

በተረፈ ከዚህ ሌላ ወይም በተጨማሪ ለማለት የሚያገለግል። *በተረፈ በሰላም እንገናኝ / በተረፈ ደብዳቤ እፅፍልሃለሁ።*

ተረፍ ስ የተረፈ ወይም የቀረ።

ተረፈ መስዋእት ስ ለመስዋእት ከቀረበ ነገር ላይ የተረፈ፥ የቀረ (ህብስት ወይም ሌላ ነገር)።

ተረፈ ምርት ስ ትርፍ ምርት።

ትሩፋት ስ ለፅድቅ ተብሎ የሚሰራ መልካም ስራ፤ በጎ አድራጎት።

ትራፊ ቅ 1. ቀሪ፡ የተረፈ። ስ 2.ፍርፋሪ፡ ቁርስራሽ፥ ከመብል የተረፈ (እንጀራ፥ ዳቦ፡...)።

ትርፍ ቅ 1.አብላጫ፡ ከሚፈለገው በላይ ሆኖ የሚገኝ። 2. ቀሪ። ስ 3. ከአንድ ነገር የሚገኝ ውጤት። 4. በሽያጭ ወይም በንግድ ከሚገኘው ገቢ ዋናውን ወይም ወጪውን ከቀነሱ ወይም ከመለሱ በኋላ የሚቀረው ገንዘብ። 5. ጥቅም።

ትርፍ ንግግር የማያስፈልግ፡ የሚያጣላ መጥፎ ንግግር።

ትርፍ ሰአት ስ 1. ከተመደበው የስራ ሰአት በላይ የሆነ የስራ ጊዜ። 2. ለማንኛውም የስራ አይነት ከተመደበው ሰአት ውጪ ያለ ጊዜ።

ትርፍ አንጀት ስ 1. በትልቁ አንጀት መጨረሻ ላይ ተቀጥሎ የሚገኝ አጭርና ቀጭን የሆነ የአንጀት ቅጥያ። 2. ትርፍ አንጀት የተባለው የሰውነት ክፍል በሽታ ወይም ህመም።

ትርፍ የኩል/የጋራ ስ ከንግድ ስራ ወይም ሽያጭ የሚገኘውን ትርፍ በጋራ እኩል ለመከፋፈል የሚደረግ ስምምነት፡ ውለታ።

የትርፍ ትርፍ ስ 1. አንድ ትርፍ እንደዋና (ካፒታል) ሆኖ ስራ ላይ ውሎ የሚያስገኘው ሌላ ትርፍ። 2. ከመጠን ያለፈ ብዙ ትርፍ።

ትርፍራፊ ቅ የተራረፈ፤ ፍርፋሪ፡ ቁርስራሽ።

ትርፍርፍ አለ ግ ሞላ፡ ተንቸረፈፈ፤ በጣም ብዙ ሆነ።

ተራረፈ ግ በብዛት ተረፈ፥ ቀረ።

የተራረፈ ቀሪ የሆነ፡ የተመለሰ (ምግብ ወይም ሌላ ነገር)።

ተትረፈረፈ ግ ከልክ አለፈ፥ በጣም በዛ፡ ከበቂ በላይ ሆነ።

አተረፈ ግ 1. ከንግድ፡ ከሽያጭ ትርፍ አገኘ። 2. ትርፍ አስገኘ። 3. አጋጠመ፡ አመጣ፥ አገኘ፥ ውጤት አስከተለ። *ባንድ ባለመርጋቱ በሽታ አተረፈ / በመልካም ስራው መልካም ስም አተረፈ።* 4. አዳነ (ከአደጋ፡ ከመጥፎ አጋጣሚ)።

አትራፊ ስ 1. የችርቻሮ ነጋዴ። ቅ 2. ትርፍ የሚያስገኝ።

አታረፈ ግ አባለጠ፥ አዛነፈ (ልብሱን)።

አትረፈረፈ ግ በጣም አበዛ፥ በብዛት አቀረበ፥ ከልክ አሳለፈ።

ተረፈሰ ግ 1. አፈሰ፡ አብዝቶ ዘገነ። 2. ቃመ። 3. በስፋትና በፍጥነት ተራመደ።

***ተረፈፈ**

ተንተረፈፈ ግ ተንደረበበ፥ ሞላ።

አንተረፈፈ ግ አንደረበበ፡ ሞላ።

ተረፍ "ተረፈ" ስር ተመ.

ተራ ስ 1.ረድፍ፡ ሰልፍ፥ ተርታ፥ መደዳ፡ መስመር። 2. ወረፋ፡ ቅደም ተከተል። 3. ተመሳሳይ ሸቀጦችን የሚያቀርቡ ወይም ተመሳሳይ የንግድ ሥራ የሚሰሩ ነጋዴዎች በመደዳ ተሰባስበው የሚገኙበት አካባቢ፥ ሰፈር። *ሸንኩርት ተራ።* ቅ 4. ሹመት፥ ማእረግ የሌለው። 5. ደረጃው ዝቅ ያለ፡ መናኛ።

በተራ 1. በመደዳ፥ በሰልፍ። 2. በወረፋ፡ አንድ በአንድ።

ባለተራ አንድ ነገር ለማድረግ ወረፋ የደረሰው።

ተራ መጣ በቅደም ተከተል፥ በረድፍ በረድፍ ሆነ፡ ተሰለፈ።

ተራ ሰጠ 1. አንድ ነገር ለማድረግ ለሌላው ሰው እድል፡ ወረፋ ሰጠ። 2. በቅደም ተከተል አስቀመጠ፡ ወረፋ አስያዘ።

ተራ ያዘ በቅደም ተከተል ወይም እንዳመጣጡ ከተሰለፈው ወይም ከተደረደረው በመቀጠል ቦታ ያዘ።

ተራ ደረሰው ለመስራት፥ ለመውሰድ ወይም አንድ ነገር ለማድረግ ወረፋው ወይም ተራው ሆነ።

ተራ ገባ በወረፋ ለመስራት፥ ለማድረግ ተሰለፈ፡ ተዘጋጀ።

ተራ ጠበቀ ወረፋ እስኪደርሰው ቆየ።

ተራ ቁጥር ስ 1. ቅደም ተከተልን የሚያሳይ ወይም በቅደም ተከተል ያለ ቁጥር። 2. አንድ ሰው ወይም ነገር የያዘውን ተራ የሚያመለክት ቁጥር።

ተራ ንግግር 1. ፍሬ ነገር ወይም ቁም ነገር የሌለው አነጋገር። 2. መደበኛ ወይም ያደባባይ ያልሆነ አነጋገር፡ ወሬ።

ተራ ወታደር ስ ወታደራዊ ሹመትና ማእረግ ያልተሰጠው የፖሊስ ወይም የመከላከያ

ስራዊት አባል።

ተረኛ ቅ ባለወረፋ፥ ባለተራ፣ ባለፋንታ።

ተራራ ስ ከአካባቢው መሬት በጣም ከፍ ብሎ የሚገኝ የመሬት አካል፣ ትልቅ ጉብታ።

ተራራ ያህላል 1. ትልቅ ወይም ግዙፍ ነው። 2. ብዙ ነው (እዳ፥ ችግር፣...)።

***ተራመሰ**

ትርምስ ስ 1. ግርግር፥ ሽብር፣ ሁከት፣ ብጥብጥ። 2. ምስቅልቅል ያለ ሁኔታ።

ትርምስምስ ስ 1. ብዙ ግርግር፣ ሽብር፣ ብጥብጥ። 2. ምስቅልቅል።

ትርምስምሱ ወጣ ተደበላለቀ።

ትርምስ አለ ግ ተመሳቀለ፥ ድብልቅልቅ አለ።

ትርምስምስ አለ ግ ተመሰቃቀለ፣ ተደበላለቀ፣ ስርአት አጣ።

ተተራመሰ ግ 1. ተሸበረ፣ ተበጠበጠ። 2. ተመሰቃቀለ።

ተተረማመሰ ግ 1.ተሸበረ፥ ታወከ፥ ተበጠበጠ። 2. ተበጣበጠ። 3. ተመሰቃቀለ።

አተራመሰ ግ 1. በጠበጠ፥ አሸበረ። 2. አመሳቀለ፣ አደበላለቀ።

አተረማመሰ ግ 1. በጠበጠ፥ አሸበረ። 2. አመሰቃቀለ፥ አደበላለቀ።

***ተራሰ**

ትራስ ስ በመኝታ ላይ ራስን ለማሳረፍ የሚያገለግል እንደ መከዳ፣ ብርኩማ ያለ ወይም ሞላላ ቅርፅ እንዲኖረው ተደርጎ በተዘጋጀ ከረጢት ውስጥ ጥጥ ወይም ስፖንጅ ወይም ሌላ ለስላሳ ነገር ተሞልቶበትና ተሰፍቶ የሚዘጋጅ ድጋፍ።

ትራስጌ ስ በመኝታ ጊዜ ራስ ወይም ጭንቅላት የሚውልበት ወይም የሚያርፍበት የትራስ ቦታ፥ አቅጣጫ፤ "ራስጌ"ም ይባላል።

ተንተራሰ ግ 1.ራሱን በትራስ ወይም በሌላ ድጋፍ ላይ አድርጎ ተኛ። 2.መሰረት አደረገ፣ ተደገፈ። *የተፈጠረውን አለመግባባት ተንተርሶ የተላለፈው ውሳኔ ትክክል አይደለም።*

አንተራሰ ግ 1.የሌላን ሰው ራስ በትራስ ወይም በሌላ ድጋፍ ላይ አሳረፈ። 2. መሰረት አደረገ፥ አስደገፈ። *የደረሰውን ኪሳራ አንተርሶ ድርጅቱን ዘጋ።*

ተራቢ "ተረበ" ስር ተመ.

ተራች "ተረተ" ስር ተመ.

ተራኪ "ተረከ" ስር ተመ.

ተራክቦ "*ረከበ^1" ስር ተመ.

ተራዳ ስ የድንኳን ምሰሶ።

ተራድኦ "ረዳ" ስር ተመ.

ተሬ ስ 1. ከአካባቢው መሬት ከፍ ብሎና ተያይዞ አግድም የሚሄድ የመሬት አካል፣ ተረተር። 2. በተራራ፣ በተረተር ላይ አግድም ተያይዞ በመደዳ የሚገኝ ዛፍ፥ ደን። 3. የቀረው ወገን ተላጭቶ ከግንባር እስከ መሃል ራስ ድረስ በቀጭኑ የሚቀር የወንድ ልጅ ፀጉር(ስእሉን ፀጉር አሰራር ስር ተመ.)።

ተርብ ስ 1.ተናዳፊና መርዘኛ የሆነ በራሪ ነፍሳት፤ የውሻ ንብም ይባላል። 2. (ዘይ.) ነገረኛ፣ ተንኳሽ።

ተርቡት ቅ ነገረኛ፣ ጠቅሜቃ (ሴት)።

የተርብ እንጀራ ስ ተርብ የሚሰራው የማር እንጀራ የሚመስል ክዳ።

ተርታ ስ 1.ረድፍ፣ መደዳ። 2. ወረፋ። ቅ 3. ሹመት፥ ማእረግ የሌለው። 4.መናኛ።

በተርታ በመደዳ፥ በሰልፍ።

ተርጓሚ "ተረጎመ"ስር ተመ.

ተርፏ

ተርፏ ተርፏ አለ በድንጋጤ ተሸበረ (ስሜት)። *ሆዷ ተርፏ ተርፏ አለ፤ ምን እንደሚያስጨንቃት እንጃ።*

ተሰባ ግ መረዳት፥ ማወቅ ተቻለ። *ነገሩ አሁን ተሰብቶኛል።*

ተሰባኝ ነገሩ ገባኝ፥ ተረዳሁት።

***ተሰተሰ**

ተስታሳ (ተሰተስ) ቅ ቀስቷሳ፥ ፈሪ።

ተንተሰተሰ ግ ፈራ።

አንተሰተሰ ግ አስፈራራ።

ተሰጥኦ "ሰጠ" ስር ተመ.

ተሲያት "ስአት" ስር ተመ.

ተሳልቆ "*ሰለቀ" ስር ተመ.

ተሳቢ "ሳበ" ስር ተመ.

ተሳቦ ስ ቀንድአውጣ ወይም ትል።

ተሳትፎ "ሰተፈ"ስር ተመ.

ተሳነ ግ አቃተ፥ አቅም የሌለው ሆነ (አንድ ነገር ለማድረግ)። *ከህመሙ የተነሳ መናገር ተሳነው።*

ተሰቦ ስ ተላላፊ በሽታ፤ ወረርሽኝ።

ተስፋ ስ 1. ይገኛል፣ ይፈፀማል፥ ይሆናል፥ ይደረጋል ተብሎ የሚጠበቅ ፥ ምኞት። 2. አለኝታ። 3. አነስተኛ ሙልሙል፣ ጢቢኛ (በቤተክርስቲያን ለነዳያን የሚሰጥ)።

ተስፋ ሰጠ 1. ለመፈፀም ቃል ገባ። 2. አፅናና፣ አበረታታ።

ተስፋ ቆረጠ የተሻለ ነገር እንደማይገኝ

ወይም እንደማይመጣ አመነ፡ ምኞቱን፥ ኣለኝታውን ከሃሳቡ ሰረዘ፥ ተወ።

ተስፋ ኣደረገ 1. አንድ ነገር እንደሚገኝ፥ እንደሚሆን፥ እንደሚፈፀም ኣሰበ፥ ገመተ፥ ጠበቀ፥ ተማመነ። 2. ኣለኝታ ኣደረገ።

ተስፋ ኣገኘ (አንድ ነገር) ይሆንልሃል፥ ይፈፀምልሃል ተባለ ወይም እንደሚሆንለት ከሁኔታዎች ገመተ፥ ተማመነ።

ተስፋ የለውም 1. ፍላጎቱን፥ ምኞቱን፥ እቅዱን ለመፈፀም ወይም ለማግኘት አይችልም። 2. አይድንም፥ አይተርፍም (ከሞት፥ ከበሽታ፥ ከአደጋ፥...)።

ተስፋ ጣለበት በአንድ ነገር ላይ እምነት ኣሳደረ፥ ተማመነ።

ተስፋ ቢስ ከንቱ፥ ወደፊት ደህና ነገር የማይጠብቀው ወይም የማይጠብቅ።

ተስፈኛ ስ በአዳሪ ትምህርት ቤት አካባቢ ከተማሪዎች የሚተርፈውን ምግብ እየተመገበ የሚኖር ቀጎኛ ተማሪ።

ተሸ

ተሸ ኣለ ግ የመቃጠል፥ የመጠበስ፥ የመፍላት፥...ድምፅ ሰጠ።

ተሽሞረሞረ ግ በልዩ ልዩ ጌጥ ተዋበ፥ ተሽቀረቀረ።

ተቀምጦ ስ ፍሬው ብዙ የሆነ ቁመቱ አጭር የማሽላ አይነት።

ተቀብኦ ስ የተፈጥሮ ስጦታ (እንደ ግርማ ሞገስ፥ በሰው የመወደድ፥ የመከበር፥ የመሳሰለው)።

የተቀብኦ ስም ስ የሹመት ወይም የማእረግ ስም (የንግስና፥ የጵጵስና፥...)።

ተቀናቀነ ግ ተፎካከረ፥ ተሻኮተ፥ ተጋፋ (የሌላውን ይዞታ ለመንጠቅ)።

ተቀናቃኝ ቅ ባላንጣ፥ ተፎካካሪ።

ተቃውሞ "***ቀወመ**" ስር ተመ.

ተቅማጣም "***ቀመጠ**" ስር ተመ.

ተቅማጥ ዝ.ከ.

ተቋም "**ቆመ**" ስር ተመ.

ተበተ(ተቤተ፥ታበየ) ግ ኩራ፥ ተጀነነ፥ ሰው ናቀ፥ በትእቢት ተሞላ።

ትእቢት ስ ኩራት፥ ንቀት፥ ማንአለብኝነት።

ትእቢተኛ ቅ ኩራተኛ፥ ሰውን የሚንቅ።

ኣተበተ ግ ኣኩራ፥ ትእቢተኛ ኣደረገ።

ተበተበ ግ 1. ብዙ ቦታ ላይ ኣሰረ፥ ጠመጠመ፥ ጠላለፈ። 2. ከበበ፥ ያዘ። 3. በአስማት፥ አዚም በማድረግ፥ በድግምት ኣሰረ፥ አፈዘዘ፥...። 4.ነገር ቋጠረ፥ ዶለተ፥ ኣሴረ።

ተብታቢ ቅ 1. መተተኛ፥ ጠንቋይ፥ አስማተኛ። 2. መሰሪ፥ ሴረኛ፥ ነገረ ሰሪ።

ትብትብ ቅ የታሰረ፥ የተተበተበ፥ የተጠላለፈ፥ የተቆላለፈ (ነገር)።

ትብትብ ስ ዝብዝብ፥ ኣተካራ።

ተተባተበ ግ ተሳሰረ፥ ተጠላለፈ፥ ተቆላለፈ፥ ተወሳሰበ።

***ተበተበ**^{1}

ተብታባ ቅ ኣፉ የሚተሳሰር፥ በትክክል የማይናገር፥ ኮልታፋ።

ተንተባተበ ግ ሲናገር ኣንደበቱ ተሳሰረ፥ ተኮላተፈ።

ኣንተባተበ ግ ኣፍን ያዘ፥ ኣሰረ፥ ኣኮላተፈ።

***ተበተበ**^{2}

ተንተበተበ ግ እሳት በደንብ ሳይገባው እስኪንጣጣ ድረስ ብቻ ተቆላ፥ በዝቅተኛ የመብሰል ደረጃ ታመሰ (ገብስ፥ ስንዴ፥...)።

ኣንተበተበ ግ እሳት በደንብ ሳይገባውና እስኪንጣጣ ድረስ ብቻ ቆላ፥ በደንብ ሳያበስል ኣመሰ።

እንትብትብ ቅ በዝቅተኛ የመብሰል ደረጃ የታመሰ፥ የተቆላ (ገብስ፥ ስንዴ፥...)።

ተባ ግ 1. ሰላ፥ ተሞረደ። 2. ቀለጠፈ (በንግግር)።

ትብ ቅ ስል፥ ስለት ያለው።

ኣተባ ግ ሳለ፥ ሞረደ።

ተባለ "**አለ**" ስር ተመ.

ተባእት ስ ወንዴ ፆታ።

ተባእታይ ቅ ወንዴ።

ተባይ ስ 1.እንደ ቅማልና ቁንጫ ያለ ደም መጣጭ ወይም ሰብል የሚያጠፋ ነፍሳት። 2. (ዘይ.) ቦጥቧጭ።

ተቤተ "**ተበተ**" ን ተመ.

ተብታቢ "**ተበተበ**^{1}" ስር ተመ.

ተብታባ "***ተበተበ**^{1}" ስር ተመ.

ተተገ "**ተገተገ**^{1}" ን ተመ.

ተትጎለጎለ ግ ቡልቅ እያለ በብዛት ወጣ (ጢስ)።

ተቻ ግ 1. ኣተተ፥ አስተያየት ሰጠ፥ ማስረጃ እየጠቀሰ ተናገረ። 2. ነቀፈ፥ እንቋሸሸ።

ተቺ ስ 1.ኣታች፥ አስተያየት ወይም ትችት የሚሰጥ ሰው። ቅ 2. ነቃፊ።

ትችት ስ 1.ኣተታ፥ በማስረጃ የተደገፈ አስተያየት። 2. ነቀፋ።

ተተቸ ግ 1. በማስረጃ የተደገፈ አስተያየት ተሰጠበት። 2. የነቀፋ አስተያየት ተሰጠበት።

አስተቸ ግ ነቀፋ አስከተለ፥ አስነቀፈ።

ተነበየ ግ አንድ ነገር ከመደረጉ ወይም ከመድረሱ አስቀድሞ ነገሩ ወደፊት እንደሚደረግ ወይም እንደሚደርስ በቅድሚያ ተናገረ።

ትንቢት ስ ወደፊት ይደረጋል፣ ይደርሳል፥ ይፈፀማል ተብሎ በቅድሚያ የተነገረ ቃል፤ ንግርት።

ትንቢት ተናገረ ተነበየ።

[የ]ትንቢት አንቀፅ ስ (ሰዋ.) ያልተፈፀመ ድርጊት ወይም ወደፊት የሚፈፀም ድርጊት የሚገለፅበት የግስ ቅርፅ (ለምሳሌ እንደ ይበላል፥ ይጠጣል፣... ያሉ)።

ትንቢተኛ ስ ትንቢት ተናጋሪ።

ተተነበየ ግ እንዲህ ይሆናል ተብሎ አስቀድሞ ተነገረ።

ተንተነ ግ 1. ከፋፈለ፣ ሠደበ፣ ደለደለ፥ ሸነሸነ። 2. ዘረዘረ፣ እየነጣጠለ አብራራ፣ አስረዳ።

ተንታኝ ቅ በዝርዝር አብራርቶ የሚያስረዳ፣ የሚያቀርብ።

ትንተና ስ 1. የማብራራት ወይም የመዘርዘር ተግባር። 2. ማብራሪያ፥ ዝርዝር ሃሳብ።

ትንታኔ ስ 1. የመከፋፈል፣ የመዘርዘር፥ የማብራራት ተግባር። 2. በዝርዝር ተከፋፍሎና ተብራርቶ የቀረበ ሃሳብ።

አስተነተነ ግ በአእምሮው አወጣ፣ አወረደ፥ አሰበ፥ አሰላሰለ።

አስተንታኝ ስ 1. በራ ደልዳይ፥ አከፋፋይ፥ መሪ። 2. አመዛዛኝ፣ አስተዋይ።

ተነነ ግ 1. ወደ እንፋሎትነት ተለወጠ። 2. ጨሰ፥ በነነ፣ ቦነነ። 3. ከነፈ፣ በረረ።

ተን ስ 1. እንደጢስ በአንዳንድ ነገሮች ላይ ተንቆርቁሮ የሚገኝ ውሃ፥ እንፋሎት። 2. በሙቀት ምክንያት የሚፈጠር እንደ ጭስ ያለ የፈሳሽ ነገር ብናኝ።

አተነነ ግ 1.ወደ እንፋሎትነት እንዲለወጥ አደረገ። 2. አጨሰ፥ አበነነ።

ተነከለ ግ ሸር፥ ተንኮል ሰራ።

ተንኮል ስ ሌላውን ለመጉዳት ወይም ለማታለል፣ ለማስደንገጥ፥... በዘዴ የሚከናወን ድርጊት ወይም ክፉ ስራ፤ ሸር።

ተንኮለኛ ቅ በሌላው ላይ መጥፎ ስራ የሚሰራ፥ ክፉ፤ ሸረኛ።

ተተናኮለ ግ ጠብ ለመፍጠር፥ ለመጣላት ፈለገ፤ ነገር ቆሰቆሰ።

ተነኮሰ ግ ነገር ፈለገ፣ ጠብ አጫረ።

ተንኳሽ ቅ ጠብ አጫሪ፣ ነገር ፈላጊ።

ትንኩሽት ስ 1. ጠብ አጫሪ፥ ነገረኛ፣ ቁጡ። 2. ተናካሽ የሆነ በቆላ የሚገኝ የቁጫጭ አይነት።

ትንኮሳ ስ ጠብ መጫር፣ ነገር መፈለግ።

ተተናኮሰ ግ ነገር ፈለገ፣ ተነኮሰ።

ተነፈሰ ግ 1. አየር ወደ ሳንባው እያስገባ አስወጣ። 2. እውስጥ ታምቆ የነበረው አየር ወጣ። *ጎማው ተነፈሰ*። 3. አወራ፥ ተናገረ። *እስከመቼ ዝም ትላለህ፤ ተንፍስ እንጂ*። 4. እረፍት፥ ፋታ አገኘ፤ ችግሩ፣ ስቃዩ ተቃለለለት።

ትንፍሽ እንዳትል ምንም ቃል እንዳትናገር፤ ዝም በል።

መተንፈሻ ከለከለ እረፍት ነሳ፣ ፋታ ከለከለ፤ አስጨነቀ።

ትንፋሽ ስ ከሳንባ የሚወጣ አየር።

ትንፋሹን ዋጠ 1. ሳይናገር ወይም ሳይተነፍስ ፀጥ ብሎ ቆየ። 2. ከድካሙ ጥቂት አረፈ።

ትንፋሼ እስካለ በህይወት እስካለሁ።

አስተነፈሰ ግ 1. በአንድ ነገር ውስጥ የተሞላን፥ የታመቀን አየር አስወጣ። 2 ገላገለ አሳረፈ፣ እፎይ አሰኘ። 3. አበረደ (ጥጋቡን፣ ትእቢትን)።

አላስተነፍስ አለ 1. እረፍት ነሳ፥ ፋታ ከለከለ፣ ጨነቀ። 2. አላናግር አለ፣ መናገር ከለከለ።

ማስተንፈሻ ስ በአንድ ነገር ውስጥ የተሞላን አየር፥... ማስወጫ፣ መልቀቂያ ቀዳዳ ወይም መቆጣጠሪያ።

ተነፈገ ግ ገማ፥ ሸተተ፣ ከረፋ (ከመታፈን የተነሳ)።

ትንፋግ (ትንፋግን) ስ 1. ርጥበት ካለው ቆሻሻ ነገር ላይ እንደጢስ እየሆነ የሚነሳ መጥፎ ሽታ። 2. አየር እንደልብ በማይገኝበትና በማይዘዋወርበት ቦታ የሚፈጠር የታፈነ ጠረን፥ ትንፋሽ።

ተነፋነፍ[ሱሪ] ስ ከሰውነት ጋር ልክክ የማይል በጣም ሰፊ የሆነ የረዥም ሱሪ አይነት።

ተን "ተነነ" ስር ተመ.

ተንበረክ ስ ለፀሎት በርከክ በሚባልበት ጊዜ ለጉልበት ማሳረፊያ ያገለግል ዘንድ በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የሚገኝ እንደ መከዳ ያለ ነገር።

ተንታኝ "ተንተነ" ስር ተመ.

ተንኮለኛ "ተነከለ" ስር ተመ.

ተንኮል ዝ.ከ.

ተንኳሽ "ተነኮሰ" ስር ተመ.

ተኛ ግ 1. ጎኑ ምድር ነካ ወይም ተጋደመ፣ ተዘረረ፥ ወደቀ። 2. እንቅልፍ ላይ ሆነ፣ እንቅልፍ ወሰደው። 3. ተለሸለሸ፥ ለጥ አለ

(ፀጉር፥ ጢፍ፥...)። 4. በግብረ ስጋ ተገናኘ። 5. ረጋ፤ አንድ ቦታ ተቀመጠ። *ሜዳው ላይ ውሃ ተኝቶበታል።* 6. መስራት አቆመ። *ሰአቱ ተኝታለች።* 7. መንቀሳቀስ ወይም አንድን ስራ ማንቀሳቀስ ተወ። 8. አዘነበለ፤ አጎነበሰ፤ ተንጋደደ።

መኝታ ስ 1. በእንቅልፍ፤ በድካም፥ በህመም፤... ጊዜ ሰውነት የሚያርፍበት፤ የሚጋደምበት ቦታ፤ አልጋ፥ መደብ፤...። 2. አልጋ ላይ መጋደም፤ መተኛት። *ሰነፍ ሰው መኝታ ያበዛል።*

መኝታ ቤት ስ ለመኝታ ወይም ለመተኛ እንዲሆን የተዘጋጀ ክፍል።

አስተኛ ግ 1. አጋደመ፤ ዘንበል አደረገ። 2. መተኛት አስቻለ። *አልጋው ለስት ሰው ያስተኛል።* 3. እንቅልፍ አስወሰደ። 4. ወዘፈ (ስራን)። 5. ጠብን ወይም ነገርን አበረደ፤ አረገበ።

ተኛ ግስ ወይም ስም በሆኑ በአንዳንድ ቃላት ላይ በስተመድረሻ በኩል እየተከሰ ሌሎች ስሞችን ወይም ቅፅሎችን ለመመስረት የሚያገለግል ምእላድ። *በላተኛ/ቀለዘተኛ/ዝምተኛ።*

ተአማኒ "አመነ" ስር **"ታማኝ"**ን ተመ.

ተአምር(ታምር) ስ አስደናቂ ፤ አስገራሚ፤ ልዩ የሆነ ነገር። "ታምራት"ም ይባላል።

ተአምረኛ ቅ ተአምር የሚሰራ፤ ልዩ ችሎታ ያለው።

ተአቅቦ "*አቀበ" ስር ተመ.

ተከለ ግ 1. የተክልን ፍሬ፥ ዘር ወይም የችግኝን ስር ከአፈር ውስጥ አስገባ፤ ሻጠ፤ ሸጎጠ፥ ቀበረ (እንዲለማ፤ እንዲፀድቅ፤ እንዲበቅል)። 2. ቸከለ። 3. ሰራ፥ መሰረተ፤ አቆመ (ቤተክርስቲያንን ወይም ሌላ ድርጅትን)። 4. ጣለ፤ ፈጠፈጠ። *መሬት ላይ በራሱ ተከለው።* 5. ሰጠ፥ አፀና፥ አስያዘ (መሬትን፤ ስራን፤...)። 6. መደበ፤ ደነባ (ግብርን፤ ስርአትን፤...)።

ተከል ነቀል ተዘዋዋሪ፤ በተወሰነ ቦታ ፀንቶ የማይቀመጥ።

ተካይ ነቃይ ስ ሺሚ ሻሪ፤ ርስት ለመስጠትና የተሰጠውንም ለመንጠቅ የሚችል የቀድሞ ጊዜ ባለስልጣን።

ተክል ስ 1. ልምላሜ ያላቸው የእፅዋት ዝርያዎች በጠቅላላ የሚጠሩበት ስም። 2. ሰው ይሆንኝ ብሎ ተክሎ የሚንከባከበው እንደ ጌሾ፤ ጎመን፥ አበባ ያሉ የሚበሉ ወይም የማይበሉ እፅዋት አጠቃላይ ስም። "አትክልት"ም ይባላል።

አትክልት(አታክልት) ስ 1. ለምግብነት የሚያገለግሉ እንደጎመን፤ ድንች፤ ቀይ ስር የመሳሰሉ የእፅዋት ዝርያዎች። 2. የ "ተክል" ን 2ኛ ፍቺ ተመ.

አትክልት ሻጭ ስ በፍራፍሬ፤ በአትክልት ንግድ ስራ ላይ የተሰማራ ነጋዴ።

አትክልተኛ ስ አትክልትን በመትከልና በመንከባከብ ሙያ ላይ የተሰማራ ሰራተኛ።

ትክል ቅ የተተከለ፤ የቆመ።

ትክለ መልካም አቋመ መልካም፥ ያማረ (ብዙውን ጊዜ ለሴት)።

ትክለ ሰውነት ስ 1. አቋም፥ የሰውነት ቅርፅ። 2. የአንድ ሰው አጠቃላይ የማንነቱና የባህርዩ ሁኔታ።

ትክል ድንጋይ ስ በመቃብር ላይ ወይም በሌላ ቦታ ሆን ተብሎ ለምልክት የተተከለና ቅርፅ ያለው ድንጋይ።

ትክለኛ ስ በቀድሞ ዘመን ከመንግስት በቋሚ ባለቤትነት ርስት ወይም መሬት የተሰጠው፤ ባለቀላድ፤ "ተተካይ" ም ይባላል።

ተተከለ ግ 1. እፅዋት፤ ተክል፥ ፍራፍሬ፤...እንዲበቅል፤ እንዲፀድቅ በመሬት ወይም በአፈር ውስጥ ተሸጎጠ። 2. ወደቀ፤ ተፈጠፈጠ። *ባፍጢሙ ተተከለ።* 3. ተመሰረተ፤ ተቋቋመ። 4. ተመደበ(ግብር፥ በጀት፤...)።

ተከተከ ግ 1. ጠቀጠቀ፤ ጨቀጨቀ፤ መሳልሶ ወጋ። 2. ጥሬን እየለቀመ በላ (ዶሮ፤ ወፍ፤...)።

ትክትክ ቅ የተወጋጋ፤ የተበሳሳ፥ የተጠቀጠቀ።

***ተከተከ**

ትክትክ አለ ግ በጣም ፈልቶ በሰለ፤ ተንተከተከ (ወጥ፤ አጥሚት፤...)።

ትክትክ አደረገ ግ በጣም አፍልቶ አበሰለ፤ አንተከተከ (ወጥን፤ አጥሚትን፤...)።

ተንተከተከ ግ በጣም ፈላ፤ በሰለ።

አንተከተከ ግ በጣም አፈላ፤ አበሰለ።

እንትክትክ ስ አጥሚት፤ ሙቅ።

ተከነ ግ 1.በጣም ተንተከተከ፤ በሰለ (ውሃ ብዙ የሌለበት ወጥ)። 2. ተናደደ፤ በገነ።

ትክን አለ ግ 1. በጣም በሰለ (ውሃ ብዙ የሌለበት ወጥ)። 2. በጣም ተናደደ።

ትክን ያለ ወጥ (ውሃ ሳይበዛበት) በደንብ የበሰለና የጣፈጠ ወጥ።

ተትከነከነ ግ በሃዘን፤ በብስጭት፤ በንዴት ተብሰለሰለ።

አትክን(አትካኝ) ቅ አብሻቂ፤ አናዳጅ።

አትከነከነ ግ በሃዘን፤ በብስጭት፥ በንዴት አብሰለሰለ።

ተከዘ ግ 1. በሃሳብ ተዋጠ፤ አዘነ፥ ቆዘመ። 2. ዋናው እስኪመጣ ድረስ ለጊዜው ሌላ ነገር ይዞ አዘገመ፤ ጠበቀ። *ምግብ እስኪቀርብ በዚች ቆሎ*

ተከዝ።

መተከዣ ስ መቆያ።

ትካዜ ስ ሃዘን፥ ቁዘማ፥ በሃሳብ መዋጥ።

ትካዜ ገባው በጭንቀት፥ በሃሳብ ተዋጠ።

ተኩላ ስ ክብና ሰፋፊ ጆሮዎች ያሉት፥ ትልቅ ውሻ የሚያክል፥ በዋሻ፥ ጥቅጥቅ ባለ ሳር ወይም በጉራንጉር ውስጥ የሚኖር ስጋ በል የሆነ የዱር እንስሳ (ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።

ተኩስ "**ተኮሰ**" ስር ተመ.

ተካ ግ 1.በጠፋ፥ በተወሰደ፥ በሄደ ነገር ፋንታ ሌላ ሰጠ፥ አመጣ፥ መለሰ፥ ከፈለ። 2.ወከለ። 3. በሌላ ሰው ወይም እቃ ፋንታ ገባ፥ አገለገለ።

መተኪያ ስ በአንድ ነገር ፋንታ በተመሳሳይ ሁኔታ የሚያገለግል፥ መለወጫ።

መተኪያ የሌለው በእሱ ፋንታ ሊሆን፥ ሊገባ፥ ሊያገለግል የማይችል ምትክ፥ ልዋጭ የማይገኝለት፥ ብቸኛ የሆነ።

ምትክ ስ 1. ተተኪ። 2. ልዋጭ።

በምትኩ 1. በፋንታው። *ተፈላጊው እቃ ስለጠፋ በምትኩ ሌላ ገዛሁ።* 2. በሰውነቱ። *እሱን ስለነኘና በምትኩ ይሄን አስተሃለሁ።*

ትክ ስ ምትክ።

ተተካ ግ 1. በጠፋ፥ በተወሰደ፥ በሄደ ነገር ፋንታ ሌላ ተሰጠ፥ ተመለሰ፥ ተከፈለ። 2. በሌላ ነገር ፋንታ መጣ፥ ገባ፥ አገለገለ። 3. ተወከለ።

ተተኪ ቅ በአንድ ሰው ወይም ነገር ፋንታ ተተክቶ የሚገባ ወይም የሚመጣ ቀጣይ፥ ተከታይ።

ተተኪ ትውልድ ካለው ትውልድ ቀጥሎ የሚመጣ አዲስ ትውልድ።

ተካሬስ(አተካሬስ) ስ በቀሚስ ላይ የሚሰፋ ወፈር ያለ መታጠቂያ ወይም መቀነት።

ተካነ "**ካነ**" ስር ተመ.

ተክሊል ስ 1. የቤተክህነት ሰዎች፥ የነገስታት ቤተሰቦች በበአል ቀን ወይም ሙሽሮች በቤተክርስቲያን ጋብቻቸውን ሲፈፅሙ ራሳቸው ላይ እንደቆብ የሚደፉት ከብር፥ ከወርቅ፥... የሚሰራ የክብር ወይም የማእረግ ምልክት (የ"**አክሊል**"ን ስእል ተመ.)። 2. በኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን አማካኝነት የሚፈፀም ስርአተ ጋብቻ።

ተክሊል አደረገ በስርአተ ተክሊል አገባ።

ተክል "**ተከለ**" ስር ተመ.

ተኮረ ግ ትክ ብሎ አየ፥ ተመለከተ፥ አስተዋለ።

ተኳር ቅ አተኩሮ የሚመለከት፥የሚያስተውል።

ትኩረት ስ አፅንኦት፥ ሃሳብን በይበልጥ አንድ ነገር ላይ ማሳረፍ።

ትኩረት ሰጠ (ለጉዳዩ) ከፍ ያለ ግምት ሰጠ፥ ይበልጥ አሰበበት።

ትኩረት ሳበ የሰው ሃሳብ ወደእሱ እንዲሆን አደረገ።

ትኩረት አገኘ ይበልጥ ታሰበበት።

ትኩር ብሎ አየ አተኩሮ ተመለከተ።

ተተኮረ ግ ትኩረት ተደረገበት፥ በደንብ ታየ። *በዚህ ጉዳይ ላይ ለምን እንደተተኮረ አልገባኝም።*

አተኮረ ግ 1. አይኑን በአንድ ነገር ላይ ተክሎ፥ አስተውሎ ተመለከተ። 2. ሃሳቡን በሙሉ ወደ አንድ ነገር ላይ አደረገ።

አትኩሮት ስ አፅንኦት፥ ትኩረት።

ተኮሰ ግ 1. አቃጠለ፥ ለበለበ፥ ፈጀ። 2. በጣም ተፋጀ፥ ከመጠን በላይ ሞቀ። 3. በጣም ሞቀ(ሰውነት)። 4. በጋለ ብረት ጠበሰ(ገላን)። 5. በካውያ ዳመጠ፥ ለመጠጠ፥ አስተካከለ (የተጨማደደ ልብስን)። 6. በሙቀት ሃይል በሚሰራ መሳሪያ እየጠቀለለ፥ እያስተካከለ አሰዋበ (ፀጉርን)። 7. በግንብ ድንጋዮች መጋጠሚያ ላይ የሚገኘውን ቦታ በሲሚንቶ እየመረገ ዳመጠ፥ ለመጠጠ። 8. መሳሪያን ወይም እንደሮኬት፥ ሚሳይል የመሳሰሉ ሩቅ የሚሄዱ ተወርዋሪ ነገሮችን አስፈነጠረ፥ ሰደደ። 9. በመሳሪያ (በጠመንጃ፥በሽጉጥ፥...)ጥይትን ወደፊት አስፈነጠረ፥አበረረ። 10.(ዘይ.) ፈፀመ፥ አከናወነ (ጉዳይን)።

መተኮሻ ስ 1. በእሳት ወይም በኤሌክትሪክ ሃይል አግሎ አንድን ነገር ለመተኮስ የሚያገለግል እንደ ብረት ዘንግ፥ ሽቦ ያለ ነገር ወይም መሳሪያ። 2. ካውያ። 3. ኢላማ።

ተኩስ ስ 1.የእሳት ጠባሳ ምልክት። 2. በጦር መሳሪያ የመተኮስ ወይም የመታኮስ ሁኔታ። 3. ከጦር መሳሪያ የሚወጣ የጥይት ድምፅ። 4. በካውያ የተተኮሰ ልብስ እጥፋት፥ የአተኳኮስ ሁኔታ።

ተኩስ ከፈተ በሌላ ወገን ላይ የጦር መሳሪያ መተኮስ ጀመረ።

የተኩስ ልውውጥ በተለያዩ ወገኖች መካከል በመሳሪያ የሚደረግ የተኩስ ምልልስ፥ ውጊያ።

የተኩስ አቁም ስምምነት በተኩስ ወይም በውጊያ ላይ ያሉ ወገኖች፥ ባሉበት ሁኔታ ላይ እንዳሉ ውጊያውን ለማቆም የሚያደርጉት ጊዜያዊ ስምምነት።

ተኳሽ ቅ 1. አንድን መሳሪያ ለመተኮስ የተመደበ ሰው። 2. ተኩሶ ኢላማውን ሳይስት የመምታት ችሎታ ያለው ሰው፥ አነጣጣሪ።

ትኩስ ቅ 1.ሙቀት ያለው፥ ገና ከእሳት ላይ የወረደ። 2. አዲስ፥ ለጋ።

በትኩሱ 1.ሳይቆይ፥ ሳይዘገይ 2. ሳይበርድ፥

ሳይቀዘቅዝ።

ትኩስ ስጋ ያልዋለ ያላደረ ስጋ።

ትኩስ ዜና አዲስ ዜና፣ ከዚህ በፊት ያልተሰማ ወይም ያልተነገረ።

ትኩሳት ስ 1 ብዙ ጊዜ የህመም ምልክት የሆነና ከተለመደው መጠን በላይ የሚወጣ የሰውነት ሙቀት። 2. ወበቅ፣ ሃሩር። 3. ንዳድ፤ የወባ በሽታ። 4. ጠባሳ (የእሳት)።

ተተኮሰ ግ 1. ተጻመጠ ወይም ተስተካከለ (ልብስ በካውያ)። 2. በሙቀት ሃይል በሚሰራ መሳሪያ እንዲስተካከል፣ እንዲዋብ ተደረገ። *ልጅቷ ፀጉሯን ተተኩሳለች።* 3. ወደ ላይ ወጣ፣ ናረ (ዋጋ)። 4. መልክና ቅርፅ ተበጀለት (የግንብ መጋጠሚያ በሲሚንቶ)። 5. የጦር መሳሪያ (ጥይት፣ ሮኬት፣ ሚሳይል፣...) ተስፈነጠረ፣ ተወረወረ፣ ፈነዳ። 6. ተበየደ።

አተኮሰ ግ ሰውነት በጣም ሞቀ (ከበሽታ የተነሳ)።

አስተኮሰ ግ 1. ተኩስ እንዲከፈት አዘዘ፣ የውጊያ ወይም የተኩስ መመሪያ ሰጠ። 2. በእሳት አስጠበሰ፣ አስበየደ።

አስተኳሽ ስ ከሩቅ ቦታ ሆኖ ከከባድ መሳሪያ ተኳሾች ጋር በሬዲዮ መገናኛ እየተነጋገረ ተፈላጊውን ኢላማ፣ ቦታ የሚያስደበድብ፤ አዋጊ።

ተኳር "ተኮረ"ስር ተመ.

ተኳሽ "ተኮሰ" ስር ተመ.

ተወ ግ 1. አንድን ስራ፣ ድርጊት፣ ግንኙነት፣ ልማድ መፈፀም ወይም ማካሄድ፣...አቆመ፣ አቋረጠ፣ ከማድረግ ተቆጠበ። 2. ይዞት፣ ጨብጦት የነበረውን ነገር ለቀቀ። 3. አንድን ነገር ችላ አለ፣ ትኩረት የማይሰጠው ሆነ። 4. ገደፈ፣ አስቀረ፣ ጣለ። 5.ይቅር አለ፣ ማረ። 6. ለቀቀ(ህመም)። *7.በአካባቢው መታየቱ፣ መገኘቱ ቀረ። ሰፈሩን ትቶታል።*

ተወኝ እባክህ አታስቸግረኝ፤ አትጨቅጭቀኝ፣ ... ለማለት የሚነገር።

ተተወ ግ 1. ተገደፈ፤ ቀረ፣ ተጣለ፤ ታለፈ። 2. ተማረ፣ ይቅር ተባለ።

ተወነ ግ በተውኔት መልክ ሰራ ወይም አሳየ።

ተዋናይ ስ በትያትር ውስጥ አንድን ገፀባህርይ ወክሎ የሚጫወት፣ ትያትር የሚሰራ የጥበብ ሰው።

ተውኔት ስ በስነፅሁፍ መልክ ተዘጋጅቶና በመድረክ ላይ ለተመልካች ቀርቦ የሚታይ የስነጥበብ ውጤት፤ ትያትር።

ተዋህደ "*ዋሃደ" ስር ተመ.

ተዋናይ "ተወነ" ስር ተመ.

ተዋፅኦ ስ ከአንድ ነገር የተገኘ ውጤት (ለምሳሌ ቅቤ፣ አይብ፣...ከወተት የሚገኝ ተዋፅኦ ነው)።

ተውላጠ ስም ስ ሰዋ. በስም ፋንታ ተተክቶ የሚገባና እንደ ስም ሆኖ የሚያገለግል የንግግር ክፍል (ለምሳሌ እኔ፤ አንተ፤ እሱ፣...)።

ተውሳከ ግስ ስ ሰዋ. "እንዴት"፤ "መቼ"፣ "የት" የሚለውን ጥያቄ የሚመልስና የግስን፤ የቅፅልን ወይም የሌላ ተውሳከ ግስን ሁኔታ የሚገልፅ የንግግር ክፍል (ለምሳሌ፦ ቶሎ፣ እዚህ፣ በፍጥነት፣...)።

ተውሳክ ስ በሽታ።

ተውኔት "ተወነ" ስር ተመ.

ተዛምዶ(ተዘምዶ) "*ዘመደ" ስር ተመ.

ተዛነብ ስ ከግድግዳ ውጭ ዙሪያውን የሚገኝ፣ ዝናብ ግድግዳን እንዳይጎዳ ለማድረግ የሚያገለግል የጣራ ክፍል፤ ታዛ፤ ሰበሰብ።

ተየበ ግ በታይፕ ፃፈ።

ታይፕ ስ በወረቀት፣ በስቴንስል ላይ ለመፃፍ የሚያገለግል የፅህፈት መኪና።

ታይፕ መታ በታይፕ ፃፈ።

ተደለቀ ግ ተቀነነ፤ በዝግታ ሄደ፣ ተጀነነ።

ተዳፋት "ዳፋ" ስር ተመ.

ተድላ "ደላ" ስር ተመ.

ተገበ ግ 1. በነፋስ ሃይል የሚወነጨፍ ዝናብ ጣለ፣ ውሽንፍር ሆነ። 2. ያለማቋረጥ አካፋ፣ ችፍ ችፍ አለ።

ተግብ ስ ውሽንፍር ያለው የክረምት ዝናብ፤ ወሊስ።

ተገብሮ ግስ "ገበረ^{1}" ስር ተመ.

ተገተገ^{1}(ተተገ) ግ 1. ገረፈ። 2. ተከሰ፣ አያያዘ (በእሳት)።

ትንታግ ቅ 1. የእሳት ክፋይ። 2.(ዘይ.) ሃይለኛ፤ ቁጡ፣ ተናጋሪ፣ ምላሰኛ።

ተንተገተገ ግ በራ፣ አበራ፣ ተብለጨለጨ፣ ተብረቀረቀ።

አንተገተገ ግ አበራ፣ አብለጨለጨ፣ አብረቀረቀ።

ተገተገ^{2} ግ አጠጋግቶ በብዛት ተከለ (ችግኝን)።

ተገነ ግ ከለለ፣ ጋረደ።

ተገን ስ 1. ከነፋስ፣ ከብርድ፣...የሚከላከል የእንጨት፣ የድንጋይ፣ የዛፍ ከለላ፤ መከታ። 2. ረዳት፣ ወገን፤ መመኪያ።

ተገን አደረገ ግ 1. መከታ፣ ከለላ አደረገ። 2. አንድን ሰው መመኪያ አደረገ።

ተገድራ ስ እንደ ቀርከሃ፣ ወይራ፣...ባሉ ዛፎች ግንድ ላይ በጥገኝነት እጅብ ብሎ የሚበቅል የእፅዋት አይነት።

ተጉመጠመጠ ግ አፉን (ውስጡን) በውሃ

ኣጠበ፡ ኣፀዳ።

ተጋ ግ 1. በረታ፡ ጠነከረ፡ ከስንፍና ራቀ። 2. ኣሰበ፡ ስለ ኣንድ ጉዳይ ተጨነቀ።

ትጉህ(ትጉ) ቅ 1. ብርቱ፡ ታታሪ። 2. ንቁ፡ ኣሳቢ።

ትጋት ስ 1. ብርቱነት፡ ታታሪነት፡ ጥረት። 2. ንቁነት።

ኣተጋ ግ ኣነቃ፡ ኣበረታ፡ ጎተጎተ።

ተጋቦ "ገባ" ስር ተመ.

ተጋድሎ "ገደለ" ስር ተመ.

ተግ

ተግታ ስ የዝናብ መቆም ወይም ብራ መሆን።

ተግ ኣለ ግ 1. ቦግ፡ ብልጭ ኣለ፡ በራ። 2. ቆመ፡ ኣባራ(ዝናብ)።

ተግ ኣደረገ ግ አበራ።

ተግሳፅ "ገሰፀ" ስር ተመ.

ተግባር "*ገበረ" ስር ተመ.

ተግብ "ተገበ" ስር ተመ.

ተግታ "ተግ" ስር ተመ.

ተግዳሮት "*ገደረ" ስር ተመ.

ተጠናወተ ግ 1. ጥል ፈለገ፡ ባላጋራ ሆነ፡ ተተናኮለ፡ ተጣላ። 2. እዘውትሮ በተደጋጋሚ ኣመመ።

ተጠናወታት ኣስወረዳት፤ ጨነገፈች።

ተጣባ ግ (የክፉ ትል በሰውነት ውስጥ) መኖሩ ታወቀ፡ ታየ።

ተፈሪ ሱሪ ስ ከላይ ሰፊ ሆኖ ከጉልበቱ በታች እስከ ቁርጭምጭሚት በጠባቡ የሚወርድ ሱሪ።

ተፈተፈ ግ ላይ ላዩን በስለት ከብዙ ቦታ ላይ በጣ፡ ሰነጠረ፡ ሰነጠቀ።

ትፍትፍ ቅ 1. ከብዙ ቦታ ላይ በስለት የተወጋጋ፡ የተሸነታተረ። 2. በኩታ ወይም በነጠላ ጸር ጸር ላይ ተሰባጥሮ የተጣለና የተለያዩ ቀለማት ያሉት ጥለት።

ትፍትፉት ስ የተሰነጠቀ፡ የተሰነጠረ፡ የተበጣ የአካል ላይ ሽንትፉት።

ተተፈተፈ ግ ከብዙ ቦታ ላይ በስለት ተቆረጠ፡ ተበጣ።

***ተፈተፈ**

ተፌ ቅ ፈጣን፡ ከተፍ።

ተፍተፍ ኣለ ግ ስራን ለማከናወን በፍጥነት ወዲያ ወዲህ ኣለ።

ኣተፈተፈ ግ ፈጠነ፡ ቸኮለ፡ ወዲያ ወዲህ ኣለ (ለስራ፡ ለወሬ፡...)።

ኣተፍታፊ ቅ ወሬን ወዲያ ወዲህ የሚያመላልስ።

ተፈጥሮ "ፈጠረ^{1}" ስር ተመ.

ተፋ ግ 1. ካፉ ኣስወጣ፡ ኣስወገደ፡ እንትፍ ኣለ (ምራቅን፡ ምግብን ወይም ሌላን ነገር)። 2. ኣስመለሰ፡ ኣስታወከ። 3. ወደ ዳር ኣወጣ፡ ጣለ (ውሃ የወሰደውን ሰው ወይም እንስሳ)። 4. ኣዳነ፡ ኣተረፈ፡ ኣወጣ (ከችግር፡ ከኣደጋ፡ ከመጥፎ ኣጋጣሚ...)። 5. ወደ ውጭ መለሰ፡ ኣልወሰደ፡ ኣልቀበል ኣለ። 6. የያዘውን (ኳስ) ለቀቀ። 7. (እስክሪብቶ ወይም ብእር) ቀለሙ ገነፈለ፡ ኣፈሰሰ። 8. (ዘይ.) ጠላ፡ ኣገለለ። *ህዝብ የተፋቸው ባለስልጣናት።*

ትፋት ስ 1. ከኣፉ የወጣ ምራቅ፡ ኣክታ። 2.ትውከት።

ትፉታም ቅ 1. (ስድብ) ትውከታም (ለሰካራም)። 2. ኣነጋገሩ ያልታረመ፡ ባለጌ።

ተተፋ ግ (ዘይ.) በጣም ተጠላ፡ ተገለለ፡ እንዲወገድ ተደረገ።

ኣስተፋ ግ (ዘይ.) ኣስጨንቆ ኣስከፈለ (ገንዘብን፡ እቃን፡...)።

ተፈ "*ተፈተፈ" ስር ተመ.

ቱ የ"ተ" ፊደል ካእብ ዘር።

ቱሃን "ትሂን" ን ተመ.

ቱሊ ስ 1. (ነውር) የቂጥ ቀዳዳ፡ ቱቲ። 2. ተረፈ ኩስ።

ቱሊያም ቅ (ነውር ፡ ስድብ) ቱሊውን በሚገባ የማያፀዳ።

ቱልቱላ ስ 1. ከቀንድ ወይም ከነሃስ፡... የሚሰራ እንደጥሩንባ ድምፅ የሚሰጥ ባህላዊ የትንፋሽ ሙዚቃ መሳሪያ(ስእሉን የሙዚቃ መሳሪያ ስር ተመ.)። 2. (ዘይ.) የውሸት፡ የጉራ ወሬ ማውራት የሚወድ።

ቱልት ስ ሲቀጠቀጥ ማላጋ የሆነ ጭማቂ የሚወጣው፡ ስሩ ረዥም የሆነ የእፅዋት ኣይነት።

ቱማታ ስ ጫጫታ፡ ውካታ፡ ጩሀት፡ ረብሻ፡ ትርምስ።

ቱምቢ ስ ግንብን በትክክል ቀጥ ኣድርጎ ለመገንባት ወይም ወደ ኣንድ ወገን ኣለማዘንበሉን ለማረጋገጥ ግንበኞች የሚገለገሉበት በሲባጎ የሚንጠለጠል የቀራጭ ብረት መሳሪያ።



ቱምቢ

ቱሪስት ስ ብዙውን ጊዜ ለደስታና ለመዝናናት ሲል ልዩ ልዩ ድንቅና ታሪካዊ

ቦታዎችን በየአንዱ እየዞረ የሚያይ ጎብኚ።

ቱሪናፋ ቅ ወሬኛ፥ ጉራ የሚያበዛ።

ቱር^{1}

ቱር አለ ግ 1. ነጣ፥ ንፁህ ሆነ። 2.ነጭ ልብስ ለበሰ።

ቱር አለ ግ በረረ (ወፍ)።

ቱርኪ ቅ ፈሪ፥ ቡከን።

ቱስ

ቱስ አለ ግ 1. ተነፈሰ፥ የታመቀው አየር ወጣ (ከጎማ ወይም ከሌላ ነገር)። 2. ቀስ ብሎ በጆሮ ነገረ።

ቱስ አደረገ ግ ድምፅ ሳያሰማ ፈሱን ለቀቀ።

ቱስክ

ቱስኪያም ቅ ፈሳም።

ቱስክ አለ ግ በነነ፥ ጨሰ(ፈሰ)።

ቱስክ አደረገ ግ ፈሳ።

ቱሽ

ቱሽ አለ ግ ቱሽ የሚል ድምፅ ሰጠ፤ በተቆላ ትኩስ ባቄላ ወይም አተር ላይ ውሃ ሲጨመርበት የሚሰማውን አይነት ድምፅ አሰማ።

ቱቢት ስ 1. ለሃዘን የሚለበስ፥ ዳርና ዳሩ ጥቁር ናይሰን ጨርቅ የተመታበት ነጠላ። 2. የሃዘን ምልክት ጥቁር ጨርቅ።

ቱባ ስ 1. በጥንተ መሰረቱ ላይ ሌላ ያልታከለበት፥ ያልተቀየጠ፥ ያልተከለሰ ንፁህ ነገር። *ቶግ ፕይቅ*። 2. ያልተቀነሰ ሙሉ የድር ወይም የሹራብ ክር ጥቅል።

ቱቦ ስ ውስጠ ክፍት ሆኖ በተለያየ መጠን ከሲሚንቶ ወይም ከብረት ወይም ከፕላስቲክ፥... የሚሰራ በውስጡ እንደ ፈሳሽ ነገር፥ የኤሌክትሪክ ሽቦ ያሉትን ነገሮች ለማስተላለፍ የሚያገለግል እቃ።

ቱታ ስ በስራ ልብስነት የሚያገለግል፥ ሸሚዝና ሱሪው ከአንድ አይነት ወፈር ያለ ጨርቅ ወጥ ሆኖ ወይም ተያይዞ የተሰፋ ወይም ባለማንገቻ ሆኖ ደረት የሚሸፍን ቅጥያ ያለው ሰፊ የሆነ ሱሪ።

ቱቻ(ቱሻ) ስ ገመድ ለመስራት የሚያገለግል፥ ሳር፥ ከዚህ ሳር የሚዘጋጀው ገመድም ቱሻ ገመድ ይባላል።

ቱኒ ስ 1. (ነውር) የቂጥ ቀዳዳ። 2. ቡከን፥ ፈሪ።

ቱኒያም ቅ (ነውር፥ ስድብ) ፈሳም።

ቱኪ ስ 1. ዋና ሹም ያልሆነ እንደ ምትክ ወይም የዋናው ሹም ረዳት ሆኖ የሚያገለግል (ሰው)። 2. (ዘይ.) ወሬ አቀባይ፥ አሳባቂ።

ቱክ

ቱክ ቱክ አለ ግ ፈሳ፥ ተንደከደከ።

ቱጃር ስ ሃብታም ነጋዴ።

ቱግ

ቱግታ ስ የቁጣ፥ የንዴት ንግግር፥ ሁኔታ።

ቱግ አለ ግ 1. በፍጥነት ነደደ። 2. በሃይል ተቆጣ፥ ተናደደ። 3. አንድ ላይ ብዙ ሆኖ በቀለ።

ቱፋህ ስ ፖም

ቱፌ "ቡፌ^{1}" ን ተመ.

ቱፍ

ቱፍ አለ ግ ተፋ፥ እንትፍ አለ።

ቱፍታ "ቡፌ^{1}" ን ተመ.

ቲ - የ"ተ" ፊደል ሳልስ ዘር።

ቲማቲም ስ ውስጡ በጥቃቅን ፍሬዎችና ፈሳሽ አዘል በሆነ አካል የተሞላ፥ ድቡልቡል ወይም ሞላላ ቅርፅ ያለው፥ ሲበስል የሚቀላ፥ ቆዳው ለስላሳ የሆነ የሚበላ አትክልት፤ ተክሉም ቲማቲም ይባላል።

ቲም

ቲም አለ ግ ከአፍ እስከ ገደፉ ሞላ፤ ጢም፥ ቲፍ አለ።

ቲኬት ስ ሲኒማ ቤት ወይም ቲያትር ቤት ለመግባት፥ በአውቶቡስ፥ በባቡር፥...ለመጓዝ ወይም እቃ ለመግዛትም ሆነ ሌላ አገልግሎት ለማግኘት የሚያስችልና በላዩ ላይ አስፈላጊው መረጃ (ዋጋ፥ ተራ ቁጥር፥ ማህተም፥...) የተፃፈበት ቁራጭ ወረቀት ወይም ካርድ።

ቲኬት ቆረጠ ቲኬት ገዛ ወይም ሸጠ።

ቲኬት ቆራጭ ስ ቲኬትን የሚሸጥ ሰራተኛ።

ቲዎሪ ስ ንድፈ ሃሳብ።

ቲፍ

ቲፍ አለ ግ በጣም ሞላ።

ታ የ"ተ" ፊደል ራብእ ዘር።

ታህሳስ ስ ከህዳር ወር ቀጥሎ የሚመጣ የአመቱ አራተኛ ወር ስም።

*ታለለ

ተላላ ቅ ሞኝ፥ በቀላሉ የሚታለል።

ተታለለ ግ 1. ተሞኘ፥ ተጭበረበረ። 2. ተሸነገለ።

አታለለ ግ 1. አሞኘ፥ አጭበረበረ፥ አቄለ። 2. ሸነገለ።

ማታለያ ስ ማባበያ፥ መሸንገያ፥ መደለያ፤ ትንሽ ስጦታ።

አታላይ ቅ 1. ውሸታም። 2. እያባበለ ወይም እየሸነገለ ጉዳዩን የሚፈፅም ወይም የሚያስፈፅም፤ ሸንጋይ። ስ 3. ሌባ።

ታለ አይሰጥ ስ የከብት ስረሰር፡ አጥንት።

ታላላቅ "ተለቀ" ስር ተመ.

ታላቅ ዝ.ክ.

ታልማ ስ 1. የወተት አንጀትና የጨጓራ መገናኛ የትንሹ አንጀት ጥቅል። 2. (ዘይ.) አቅመቢስ፥ ለንቋሳ።

ታምር "ተአምር" ን ተመ.

ታምቡር ስ ጠቅላላ ቅርፁ ክብ ሆኖ ሁለት አፎቹ በቆዳ የተለበዱ፤ አብዛኛውን ጊዜ ሰልፈኞች የሚታጀቡበት፥ በአንድ ወይም በሁለት አጫጭር በትሮች እየተመታ የከበሮ ድምፅ የሚሰጥ የሙዚቃ መሳሪያ።

ታሪክ "ተረከ" ስር ተመ.

ታሪፍ ስ 1. በገቢ ወይም በወጪ ሸቀጦች ላይ መንግስት የሚጥለው ቀረጥ። 2. ሆቴሎችና ተመሳሳይ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ለምግብ ወይም ለሚሰጡት አገልግሎት የሚያስከፍሉት የተወሰነ የዋጋ ዝርዝር።

ታርጋ ስ በተሽከርካሪዎች የፊትና የኋላ አካል ላይ ተፅፎ በግልፅ የሚታይ የመለያ ቁጥር።

ታበየ "ተበተ"ን ተመ.

ታቦት ስ 1. ፅላት። 2. ፅላት የሚቀመጥበት ሳጥን፤ የፅላት ማህደር።

ታቦት ነገሰ ታቦት ከቤተክርስቲያን ወጥቶ በመንፈሳዊ ስነስርአት ተከበረ።

የታቦት ራት ስ የከተራ እለት ታቦት በሚያድርበት ቦታ ከምእመናን ለካህናቱ የሚሰጥ ምግብና መጠጥ።

ታተረ ግ ተፍጨረጨረ፥ ጣረ፥ ተጋ። *መሻሻል እንዲኖር በስራ መታተር ያስፈልጋል።*

ታታሪ ቅ ትጉህ፥ ተፍጨርጫሪ።

ታታ^{1} ግ ጠላለፈ፤ አስባበረ፤ አወሳሰበ ወይም እንደወንፊት፤ አቴና፥ መረብ ያለ ነገር ሰራ።

ትት ቅ 1. እንደወንፊት፤ መረብ፥...ጥልፍልፍ የሆነ። ስ 2. ቱባ (የድር ወይም የጥለት ክር)።

ታታ^{2}

ታታ አለ ግ ተንታታ፥ ተከታታይ የእሩምታ ተኩስ ድምፅ ሰጠ ወይም ተሰማ።

ተንታታ ግ የተከታተለ የተኩስ ድምፅ ሰጠ፥ ተሰማ፥ ተንጣጣ።

አንታታ ግ የተከታተለ የተኩስ ድምፅ አሰማ።

ታታሪ "ታተረ" ስር ተመ.

ታች መቀ. 1. ከአንድ ነገር ስር ወይም በስተግርጌ ያለ። 2. ቁልቁል፥ ዝቅተኛ የሆነ (ስፍራ፥ መንገድ፥...)።

በታች መቀ. 1. በግርጌ፤ በስር [በኩል]። 2. በቁልቁለት [በኩል]።

የበታች ቅ 1. ዝቅተኛ። 2. ከታች ያለ። 3. ታናሽ።

የበታች መኮንን ስ ከምክትል መቶ አለቃ በታች ከተራ ወታደር በላይ ሹመት ያለው ወታደር።

ከ ___በታች 1. ከ___ግርጌ ወይም ስር። 2. ከ __ቀጥሎ። *ከዚህ በታች የተዘረዘሩት፥...።* 3. ከ __ ዝቅ የሚል ወይም የሚያንስ። *ከዚህ በታች በሆነ ዋጋ ላይገኝም።*

ወደታች አለው አስቀመጠው(ተቅማጥ)።

ታችኛ ቅ 1. በስተስር፥ በስተግርጌ ያለ። 2. ዝቅ ብሎ የሚገኝ።

ታች አምና "ሃች አምና" ን ተመ.

ታኒካ ስ ገረወይና። በአንዳንድ አካባቢ እንደ ጣሳ፥ ኩባያ፥... ያሉ እቃዎችም ታኒካ እየተባሉ ይጠራሉ።

ታናሽ "አነሰ" ስር ተመ.

ታንክ ስ መላ አካሉ ብረት ለበስ የሆነ፤ የሚሽከረከርበት የብረት ሰንሰለት ወይም ጎማ ያለው፥ አስፈላጊውን ትጥቅና ስንቅ ከነወታደሮቹ በውስጡ ሸፍኖ ሊይዝ የሚችል ከባድ የጦር ተሽከርካሪ ወይም መኪና።

ታንከኛ ስ በታንክ ምድብ የጦር ክፍል ውስጥ የሚያገለግል ወታደር።

ታንኳ ስ ከቀርከሃ ወይም ከሸንበቆ ወይም ከደንገል፤... የሚሰራ የውሃ ላይ መጓጓዣ(ስእሉን መጓጓዣ ስር ተመ.)።

ታከተ ግ ሰለቸ፤ ደከመ።

አታከተ ግ አሰለቸ፥ አደከመ።

አታካች ቅ 1. አድካሚ፥ አሰልቺ የሆነ (ስራ)። 2. በጠባዩ አሰልቺ የሆነ (ሰው)።

ታኬታ ስ ለእግር ኳስ ጨዋታ የሚያገለግል፤ ስሩ(ሶሉ) መሬት ለመቆንጠጥ የሚያስችሉ የላስቲክ ወይም የብረት ጡቶች ያሉት የቆዳ ጫማ።

ታክሲ ስ በከተማ ውስጥ መንገደኞች ገንዘብ እየከፈሉ ከቦታ ወደ ቦታ የሚጓጓዙበት አነስተኛ አውቶሞቢል።

ታክሲ ያዘ/ወሰደ በታክሲ ተሳፈረ፥ ሄደ።

ታክቲክ ስ ዘዴ፤ አንድን አላማ ለመፈፀም፥ ተግባራዊ ለማድረግ የሚገለገሉበት ስልት።

ታክቲከኛ ቅ ዘዴኛ።

ታኮ^{1} ስ 1. ታኮ ጫማ፤ ባለተረከዝ ጫማ። 2. ከመሬት ከፍታ ያለው የጫማ ተረከዝ።

ታኮ^{2} ስ የቆመ መኪና እንዳይንሸራተት ጎማዎቹ ስር የሚደረግ የብረት፤ የእንጨት ወይም የድንጋይ፤... ድጋፍ።

ታወሰ ግ ትዝ አለ፥ ታሰበ (የተረሳ ነገር)።

ትውስታ ስ ትዝታ።

ትውስ አለ ግ ትዝ አለ፤ ታሰበ።

አስታወሰ ግ 1. የቆየን፥ ያለፈን፥ የተረሳን ነገር ትዝ አሰኘ፤ ትዝ እንዲል አደረገ። 2. የተረሳን ሰው ወይም ነገር ማን ወይም ምን እንደሆነ ሊያውቅ ቻለ፥ ትዝ አለው። 3. የቆየን ወይም ያለፈን ነገር እንደገና አሰበ። 4. አሳሰበ፤ እንዳይረሳ አደረገ(ሌላን ሰው)።

ማስታወሻ ስ 1. እንዳይረሳ፤ እንዳይዘነጋ፤ ትዝ እንዲል በመታሰቢያነት የሚቀመጥ ሃውልት ወይም ሌላ ነገር። 2. አንድ ነገር እንዲሰራ ወይም እንዲፈፀም የሚያሳስብ ፅሁፍ። 3. እንዳይረሳሱ፤ እንዲተሳሰቡ ወይም ፍቅርና አክብሮትን ለመግለፅ ለዘመድ፥ ለወዳጅ የሚደረግ ስጦታ። 4. ማስታወሻ [ደብተር]፤ የተለያዩ የግል ጉዳዮች፤ ነጥቦች አድራሻዎች፤... የሚፃፉበት ትንሽ ደብተር።

አስታዋሽ ቅ 1. የማይረሳ፤ ዝንጉ ያልሆነ። 2. አሳሳቢ፥ አስገንዛቢ። 3 ጠያቂ ፤ ረዳት።

ታዋቂ "**አወቀ**" ስር ተመ.

ታዘበ ግ 1. ሌላው የሰራውን መጥፎ ተግባር በማየት ቅር ተሰኘ። 2. ሁኔታዎችን በመገምገም ተመለከተ ፤ አስተዋለ።

ታዛቢ ስ 1. ተመልካች። 2. ተቆርቋሪ። 3. ምስክር፤ እማኝ።

ትዝብት ስ አንድ ሰው የሚያደርገውን መጥፎ ተግባር የመገምገም አመለካከት።

ተዛዘበ ግ አንዱ ሌላውን በመታዘብ ሁኔታ ገመገመ።

አስተዛዘበ ግ አንዱ ሌላውን (እርስ በርስ) እንዲታዘብ፤ እንዲተዛዘብ፥ እንዲገማገም፤ እንዲገማመት አደረገ።

ታዛ ስ በስተውጭ ያለ የቤት ዙሪያ ጣሪያ።

ታዛቢ "**ታዘበ**" ስር ተመ.

ታይፐ "**ተየበ**" ስር ተመ.

ታደገ ግ አዳነ፤ ቤዛ ሆነ።

ትድግና ስ መታደግ፤ ማዳን።

ታዳጊ ቅ አዳኝ፤ ቤዛ።

ታዲያ አንድን ሃሳብ ቀደም ብሎት ከተነገረው ጋር ለማያያዝ የሚያገለግል ቃል፤ የንግግር፤ የአረፍተ ነገር ማያያዣ።

ታዲያስ 1. ከዚያስ፥ እናስ እያሉ አንድ ሰው በጀመረው ነገር ወይም ገለፃ እንዲቀጥልበት፥ እንዲገፋበት ለማድረግ ከአድማጭ የሚሰነዘር ቃል። 2. "አዎን" ለማለት በቃል ንግግር ላይ የሚያገለግል ቃል። __*ጠያቂ፡*__ *ስራውን ጨረስክ ማለት ነው?* __*መላሽ፡*__ *ታዲያስ።* 3. በጣም በሚቀራረቡ ሰዎች መካከል ለሰላምታ የሚባል ቃል።

ታዳጊ^{1} "**ታደገ**" ስር ተመ.

ታዳጊ^{2} "**አደገ**" ስር ተመ.

ታጀረ ግ ከራ፤ ተጀነነ።

ታገለ ግ 1. አንዱ ሌላውን ለመጣል፤ ለማጥቃት፤...ተያያዘ፤ ተናነቀ፤ ግብግብ ወይም ትግል ገጠመ። 2. አንድን ነገር ለማከናወን፤ ለማግኘት፤... ተጣጣረ፤ ለፋ፥ መስዋእትነት ከፈለ። 3. አስቸገረ፤ በቀላሉ የማይከናወን አልሆን አለ።

ታጋይ ቅ 1.ትግል፤ ግብግብ የመግጠም ችሎታ ያለው። ስ 2. ለአላማው፤ ለእምነቱ መከበር ወይም እውን መሆን የሚታገል፤ መስዋእትነትን የሚከፍል (ብዙውን ጊዜ ለፖለቲካ አላማ)።

ትግል ስ 1.አንዱ ሌላውን ለመጣል ወይም ለማጥቃት፥... የሚያደርገው ትንቅንቅ፤ ፍትጊያ፤ ግብግብ። 2. ተግባርን፤ ስራን ለማከናወን የሚደረግ ጥረት፤ መፍጨርጨር። 3. (ብዙውን ጊዜ የፖለቲካ) አላማን ለማሳካት የሚደረግ ጥረት፤ መፍጨርጨር።

አታገለ ግ 1.አለፋ፥ አደከመ፤ በቀላሉ የማይከናወን ሆነ። 2.ትግልን መራ።

ታገሰ ግ ረጋ አለ፥፥ ሳይቸኩል በእርጋታ ጠበቀ። 2. ትንኮሳን ቻለ።

ታጋሽ ቅ ረጋ ያለ፤ ቻይ፤ የማይቸኩል፤ ቶሎ የማይናደድ።

ትእግስት ስ እርጋታ፤ መቻል፤ አለመቸኮል።

ትእግስተኛ ቅ ረጋ ያለ፤ ቻይ፤ ችኩል ያልሆነ።

አስታገሰ ግ 1. ዝም አሰኘ፤ አቀዘቀዘ፥ ረጋ እንዲል አደረገ። 2. ቀነሰ፤ አበረደ፤ ለጊዜው አቆመ (ህመምን፤ ረሃብን፥...)።

ማስታገሻ [መድሃኒት] ስ ለጊዜው ህመምን፤ ስቃይን የሚቀንስ መድሃኒት።

ታጠቀ ግ 1. በወገቡ ላይ ሸብ አደረገ፤ አሰረ (ቀበቶን፥ ዝናርን፥...)። 2. ሰበሰ (ሱሪን፤ ቀምጣን)። 3. አሸረጠ፤ አደገደገ። 4. እንደ ሽጉጥ ወይም ጠመንጃ ያለ መሳሪያ ያዘ፤ በቀላልም ሆነ በከባድ የጦር መሳሪያ ተደራጀ፥ ተዘጋጀ። 5. ተዘጋጀ፥ ተጠናቀቀ፥ ቆርጦ ተነሳ። *መሃይምነትን ለማጥፋት ታጥቀን ተነስተናል።*

መታጠቂያ ስ መቀነት፥ ቀበቶ።

ታጣቂ ስ የጦር መሳሪያ የያዘ ሰው።

ትጥቅ ስ 1. ሽርጥ፥ ድግድግ። 2. የጦር መሳሪያ። 3. አንድ ነገር ለማካሄድ (ጦርነት፤ ስራ፤ ጉዞ፥...) የሚያስፈልግ ነገር፤ ዝግጅት።

ትጥቅ ፈታ የያዘውን የጦር መሳሪያ

አስረከበ፥ ተቀማ።

ትጥቀ መልካም በአለባበሷ ጥሩ የሆነች ሴት።

ትጥቅና ስንቅ ስ ጦርነትን ለማካሄድ የሚያስፈልገው የጦር መሳሪያ፡ ቀለብና ሌላም ቁሳቁስ፤ ስንቅና ትጥቅም ይባላል።

የትጥቅ ትግል ስ በጦር መሳሪያ አማካኝነት የሚካሄድ ትግል።

አስታጠቀ ግ 1. አለበሰ (ሱሪን፥ ቁታን)። 2. የጦር መሳሪያ ሰጠ፥ አደለ፥ በጦር መሳሪያ አደራጀ። 3. (ዘይ.) ሰደበ፥ አዋረደ። *በስድብ አስታጠቀው።*

ታፋ ስ ከጭን በላይ ከወገብ በታች ከመቀመጫ በስተጎን በኩል ያለ አካል፥ ስርጎድ ያለው የሰውነት ክፍል(ስእሉን በውነት ስር ተመ.)።

ቴ የ "ተ" ፊደል ሃምስ ዘር።

ቴሌስኮፕ ስ የቱቦ ቅርፅ ያለውና ሩቅ ያሉ ነገሮችን አቅርቦና አጉልቶ የሚያሳይ መሳሪያ።

ቴሌቪዥን ስ ከቴሌቪዥን ማቢያ የሚሰራጨውን ስእል፥ እንቅስቃሴና ድምፅ ከአየር እየጠለፈ የሚያሳይና የሚያሰማ መሳሪያ።

ቴሌቪዥን ማቢያ ስ በኤሌክትሪክና በልዩ ልዩ ዘመናዊ መሳሪያ፥ ድምፅ፥ ስእልና ማንኛውም አይነት እንቅስቃሴ በአየር ውስጥ ወደተፈለገው ቦታ እንዲሰራጭ የሚያደርግ ማቢያ።

ቴሌክስ ስ መልእክትን በትየባ መልክ በሚፅፍና በኤሌክትሪክ ሞገድ አማካኝነት ወደተፈለገው ቦታ በሚያስተላልፍ ወይም በዚሁ መልክ የተሰራጨን መልእክት ተቀብሎ ወዲያውኑ በሚፅፍ መሳሪያ አማካኝነት የሚካሄድ ግንኙነት፤ መሳሪያውም "ቴሌክስ" ይባላል።

ቴሌግራም ስ በኤሌክትሪክ ሞገድ አማካኝነት የሚተላለፍ የፅሁፍ መልእክት።

ቴሌፎን "ስልክ" ን ተመ.

ቴምር "ተምር"ን ተመ.

ቴምብር ስ ተፈላጊው ቀረጥ ለመንግስት መከፈሉን እንዲያረጋግጥ በፖስታዎች፥ በደብዳቤዎች፥ በሸቀጦች፥...ላይ የሚለጠፍ፥ በላዩ ላይ የቀረጡ ዋጋና ልዩ ምልክት (አርማ) የታተመበት፤ መጠኑ አነስተኛ የሆነ በመንግስት የሚዘጋጅ ስስ ወረቀት።

ቴርሞ ሜትር ስ የሙቀት መጠን መለኪያ መሳሪያ፤ የሙቀት መጠን መለኪያ።

ቴስተር ስ በኤሌክትሪክ ሽቦ ውስጥ ወይም የኤሌክትሪክ ሃይል በሚያልፍበት እቃ ውስጥ የኤሌክትሪክ ሃይል መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ የሚያገለግል መሳሪያ።

ቴክኒክ ስ 1. ከሞተር፥ ከሜካኒክ፥ ከእንጨት ስራ ጋር የተያያዘ የእጅ ሙያ ጥበብ። 2. ዘዴ፥ ብልሃት።

የቴክኒክ ትምህርት ስ የእደጥበብ፥ የሜካኒክ፥ የኤሌክትሪክ፥... ዘርፉን የሚመለከት የሙያ ትምህርት።

ቴክኒሽያን ስ የቴክኒክ ስራዎችን የሚያከናውን ባለሙያ።

ቴክኖሎጂ ስ የሳይንሳዊ ግኝቶች በተለይ ለኢንዱስትሪያዊ ጠቀሜታ ተግባራዊ የመሆን ስልት ጥናትና እውቀት፤ ተግባራዊ ሳይንስ።

ቴፕ (ቴፕሪኮርደር) ስ በቴፕ ክር ላይ ድምፅን ለመቅረፅና የተቀረፀውንም ድምፅ መልሶ ለመስማት የሚያገለግል መሳሪያ።

የቴፕ ክር ስ ማግኔትነት ያለው፥ በቴፕ አማካኝነት ድምፅን እየቀረፀ የሚያስቀር፥ ስስ የሆነ የፕላስቲክ ጥብጣብ።

ት የ"ተ" ፊደል ሳድስ ዘር።

ትሁት ቅ ቅን፥ ታዛዥ፥ ሰው አክባሪ።

ትህትና ስ ቅንነት፥ ታዛዥነት፥ ሰው አክባሪነት፥ ራስንና የራስን ዝቅ አድራጊነት።

ትህርምት ስ መጥፎ የተባሉ ድርጊቶችን ከመፈፀም ራስን የመቆጣጠር ሃይማኖታዊ ተግባር።

ትህትና "ትሁት" ስር ተመ.

ትኋን(ቱሃን) ስ እንደቁንጫና ቅማል የሰውን ደም በመምጠጥ የሚኖር የቤት ውስጥ ተባይ።

ትኋናም ቅ (ስድብ) ትኋን ያለበት ወይም የበዛበት።

ትላም "ተላ" ስር ተመ.

ትላበራ ዝ.ክ.

ትላንት "ትናንት"ን ተመ.

ትል "ተላ" ስር ተመ.

ትልልቅ "ተለቀ" ስር ተመ.

ትልም "ተለመ" ስር ተመ.

ትልቅ "ተለቀ" ስር ተመ.

ትልታይ "ተለተለ" ስር ተመ.

ትልትላት ዝ.ክ.

ትልትል ዝ.ክ.

ትልአበራ "ተላ" ስር **"ትላበራ"** ን ተመ.

ትሙን "ተሙን" ን ተመ.

ትምህርት "*መሃረ" ስር ተመ.

ትምቡሽ

ትምቡሼ(ትንቡሼ) ቅ ድንቡሼ፥ ወፍራም።

ትምቡሽ አለ ግ ድቡልቡል አለ፤ ወፈረ።

ትምባሆ (ትንባሆ) ስ ርጥቡን ቅጠል ለጥልጠው በአፍ የሚይዙት ወይም አድርቀውና አሽተው በሲጋራ መልክ ጢሱን የሚምጉት ሱስ የሚያሲዝ እፅ።

ትምባሂም ቅ (ስድብ) ትምባሆ የሚያጤስ፥ የትምባሆ ሱስ ያለበት።

ትምትም "ተመተመ" ስር ተመ.

ትምክ

ትምክ አለ ግ ስርጉድ፥ ስምጥ አለ፥ ላላ።

ትምክ ትምክ አለ ግ ሲነኩት ስምጥ ስምጥ፥ ስርጉድ ስርጉድ አለ።

ትምክህተኛ "*መካ" ስር ተመ.

ትምክህት ዝ.ክ.

ትረባ "ተረበ" ስር ተመ.

ትሩፋት "ተረፈ" ስር ተመ.

ትራምፔት ስ ጥሩምባ የሚመስል በትንፋሽ የሚሰራ ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያ(ስእሉን የሙዚቃ መሳሪያ ስር ተመ.)።

ትራስ "*ተራሰ" ስር ተመ.

ትራስጌ ዝ.ክ.

ትራንስፎርመር ስ 1. በኤሌክትሪክ ሃይል በሚሰሩ በሬዲዮ፥ በቴፕሪኮርደር፥ በቴሌቪዥን፥… ውስጥ የሚገኝ የኤሌክትሪክ ሃይልን እየመጠነ የሚያሰራጭ መሳሪያ። 2. የኤሌክትሪክ ጋን።

ትራንስፖርት ስ መጓጓዣ መንገድ ወይም መኪና፥ አውሮፕላን፥… የመሳሰለው መገልገያ።

ትራክተር ስ የእርሻ መኪና።

ትራኮማ ስ የሚያቃጥልና የሚያሳክክ ተላላፊ የአይን በሽታ፤ አይነ ማዝ።

ትራጄዲ ስ መድረኩ በሃዘን ድባብ የተሞላ ሆኖ በዋና ገፀባህርዩ ውድቀት ወይም ሞት የሚያበቃ የትያትር አይነት።

ትራፊ "ተረፈ" ስር ተመ.

ትራፊክ ስ 1. በመንገድ ላይ የሚታየው የሰዎች፥ የተሽከርካሪዎች፥… እንቅስቃሴ ወይም በመንገድ ላይ የሚንቀሳቀሱ ሰዎች፥ ተሽከርካሪዎች፥… በአንድነት የሚጠሩበት ስም። 2. አሽከርካሪዎች የትራፊክ ደንብ የሚጠይቀውን ስነስርአት ማሟላታቸውን የሚከታተል ፖሊስ፤ ትራፊክ ፖሊስ ።

የትራፊክ ህግ/ደንብ ስ ስለተሽከርካሪዎች ደህንነት፥ ስለአሽከርካሪዎችና የመንገድ ስነስርአትን የሚመለከት በትራፊክ ፅ/ቤት የወጣ ወይም የተዘጋጀ መመሪያ፥ ደንብ፥ ህግ።

የትራፊክ መብራት ስ መስቀለኛ መንገድ ባለበት አካባቢ ተሽከርካሪዎች ተራቸውን ጠብቀው እንዲቆሙ ወይም እንዲሄዱ ምልክት የሚያሳይ ባለቀለም (አረንጓዴ፥ ቢጫ፥ ቀይ) መብራት።

ትር

ትርታ ስ ምት ንዝረት (ብዙውን ጊዜ የልብ)።

ትር ትር አለ ግ ደው ደው አለ፥ መታ ነዘረ (ብዙውን ጊዜ ልብ)።

ትርምስ "*ተራመሰ" ስር ተመ.

ትርሽም

ትርሽም አለ ግ ተሰበረ።

ትርሽም አደረገ ግ ሰበረ።

ትርታ "ትር" ስር ተመ.

ትርታሮ "ተረተረ" ስር ተመ.

ትርትር ዝ.ክ.

ትርንጎ ስ መጠኑ ከብርቱካን አነስ የሚል፥ ሽፋኑ ሳሳ፥ አካሉ ጠንከር ያለ፥ ጥሩ መአዛ ያለውና የሚበላ ፍሬ የሚያፈራ ተክል፤ ፍሬውም ትርንጎ ይባላል።

ትርኢት ስ እንደ ሙዚቃ፥ ትያትር፥ አክሮባት፥… ያለ ለህዝብ ቀርቦ የሚታይ ዝግጅት።

ትርኪምርኪ ስ 1. ቅራቅንቦ፥ ኮተት። 2. (ዘይ.) የማይረባ ነገር።

ትርክም

ትርክምክም ቅ የማይረቡ እቃዎች ስብስብ።

ትርኳሽ "ተረከሰ" ስር ተመ.

ትርጁማን ስ በአንድ ቋንቋ የተነገረን ነገር በሌላ ቋንቋ ለውጦ የሚናገር፤ አስተርጓሚ።

ትርጉም "ተረጎመ" ስር ተመ.

ትርግ

ትርግታ ስ ምት፥ ንዝረት (የልብ፥ የእርግብግቢት፥ የደምስር፥…)።

ትርግ ትርግ አለ ግ መታ፥ ተርገበገበ (ልብ፥ እርግብግቢት፥…)።

ትርጓሜ "ተረጎመ" ስር ተመ.

ትርፍ "ተረፈ" ስር ተመ.

ትስብእት ስ (ክር.) ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስጋ የለበሰበት ቀን (መጋቢት 29)።

ትቢት "ተበተ" ስር ተመ.

ትቢያ ስ ደቃቅ አፈር፥ አቧራ።

ትብ "ተባ" ስር ተመ.

ትብትብ "ተበተበ" ስር ተመ.

ትብትብ ዝ.ክ.

ትት "ታታ^{1}" ስር ተመ.

ትችት "ተቸ" ስር ተመ.

ትናንሽ "ኣነሰ" ስር ተመ.

ትናንት(ትላንት፡ትናንትና) ስ. 1. ከዛሬው ቀን በፊት የነበረው፡ ያለፈው ቀን። *ትናንትናን የማስታውስበት ብዙ የሚገርም ነገር ኢጋጥሞኛል።* 2. (ዘይ.) ከዚህ በፊት፥ ባለፈው ዘመን ወይም ያለፈው ዘመን። *ትናንት ህዝብን ሲበድሉ የነበሩ ባለስልጣናት...*

ከትናንት ወዲያ(በስቲያ) ከትናንት በፊት የነበረው ቀን።

ትናጋ(ትናግ) ስ ከኣፍ ወደ ጉሮሮ በሚወስደው መስመር ላይ ከላንቃ መዳረሻ ኣካባቢ የሚገኝ የአፍ ውስጥ የላይኛው ክፍል(ስእሉን እፍ ስር ተመ.)።

የትናጋ ድምፅ ስ (ስነል.) እንደ ቀ፥ ገ፥ ክ ያሉ የምላስን የኋለኛ ክፍል ከትናጋ ጋር በማገናኘት የሚፈጠር የንግግር ድምፅ።

ትን

ትንታ ስ የሚያፍን፥ የሚያስነጥስ፥... ወደ ሰርን ወይም ወደ አየር ቧንቧ የገባ የምግብ እኛኪ ወይም የመጠጥ ፍንጣቂ የሚያስከትለው የማፈን፥የማስነጠስ፥...ሁኔታ ።

ትን አለ ግ የምግብ እኛኪ ወይም የመጠጥ ፍንጣቂ ወደአየር ቧንቧ ወይም ወደ ሰርን በመሄድ አፍንጫን፥ ጉሮሮን ዘጋ ወይም አስነጠሰ፥ አባለ።

ትንሳኤ ስ 1.(ክር.) ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ከመቃብር የተነሳበት እለት፥ ፋሲካ። 2. ከሞት ወይም ከውድቀት በኋላ መነሳት።

ትንሳኤ ሙታን ስ (ክር.) በአጠቃላይ ሙታን ሁሉ የሚነሱበት ቀን፥ ዳግም ምፅአት።

ትንሽ "አነሰ" ስር ተመ.

ትንቡሼ "ትምቡሽ" ስር "ትምቡሼ" ን ተመ.

ትንቢተኛ "ተነበየ" ስር ተመ.

ትንቢት ዝ.ከ.

ትንባሆ "ትምባሆ" ን ተመ.

ትንተና "ተነተነ" ስር ተመ.

ትንታ "ትን" ስር ተመ.

ትንታኔ "ተነተነ" ስር ተመ.

ትንታግ "ተገተገ^{1}" ስር ተመ.

ትንኝ ስ ብዙውን ጊዜ እርጥበት ወይም ፈሳሽ ነገር ባለበት አካባቢ የምትገኝ አነስተኛ የሆነች በራሪ ነፍሳት።

ትንኩሸት "ተነከሰ" ስር ተመ.

ትንካሳ ዝ.ከ.

ትንግርተኛ "ነገረ" ስር ተመ.

ትንግርት ዝ.ከ.

ትንፋሽ "ተነፈሰ" ስር ተመ.

ትንፋግን "ተነፈገ^{1}" ስር "ትንፋግ" ን ተመ.

ትንፋግ "ተነፈገ^{1}" ስር ተመ.

ትእምርት ስ ምልክት (አንድን ሰው፥ ሃሳብ፥ አላማ፥... የሚጠቁም)።

ትእምርተ መስቀል ስ የመስቀል ምልክት።

ትእምርተ ስላቅ ስ የተጻፈው ነገር ስላቅ መሆኑን ለማሳየት የሚደረግ ምልክት። ምልክቱም ¡ ነው።

ትእምርተ ጥቅስ ስ ሌላ ሰው የተናገረው፡የጻፈው፡... መሆኑን ለማመልከት ከሚጠቀሰው ነገር መጀመሪያና መጨረሻ ላይ በሰተ ኣናት በኩል የሚደረግ ምልክት። ምልክቱም " " ነው።

ትእቢተኛ "ተበተ" ስር ተመ.

ትእቢት ዝ.ከ.

ትእዛዝ "አዘዘ" ስር ተመ.

ትእግስተኛ "ታገሰ" ስር ተመ.

ትእግስት ዝ.ከ.

ትከሻ ስ 1. ከአንገት መቆሚያ እስከ ክንድ መነቀያ (መገጠሚያ) ድረስ ያለው የሰውነት ክፍል (ስእሉን "ሰውነት" ስር ተመ.)። 2. (ዘይ.) እድል።

በ ___ ትከሻ ቡ-እርዳታ። በሰው ትከሻ ነው እዚህ የደረሰው።

ትከሻ ሰጠ/አሳየ ታበየ፥ ንቀት አሳየ፥ አልታዘዝ አለ።

ትከሻ ወረደ እስክሰታ ወረደ፥ እስክስታ መታ፥ እስክስ አለ።

ትከሻ የለውም እድል የለውም ወይም እድሉ ጥሩ አይደለም።

ትኩረት "ተኮረ" ስር ተመ.

ትኩሳት "ተኮሰ" ስር ተመ.

ትኩስ ዝ.ከ.

ትካዜ "ተከዘ" ስር ተመ.

ትክ "ተካ" ስር ተመ.

ትክ

ትክ አለ ግ ትኩር አለ፥ አይኑን አንድ ቦታ ተከለ።

ትክ ብሎ ተመለከተ ትኩር ብሎ ተመለከተ፥ አስተዋለ።

ትክል "ተከለ" ስር ተመ.

ትክትክ "ተከተከ" ስር ተመ.

ትክትክ ስ ብዙውን ጊዜ ህፃናትን የሚያጠቃ ቶሉ ቶሉ የሚያስል በሽታ።

ትክክለኛ "አከለ" ስር ተመ.

ትክክል ዝ.ከ.

ትውልድ "ወለደ" ስር ተመ.

ትውር

ትውር እንዳትል ድርሽ፡ ዝር እንዳትል። *ምንም ቢቸግርህ እነዚያ ክፉዎች ወዳሉበት አካባቢ ትውር እንዳትል።*

ትውስታ "ታወሰ" ስር ተመ.

ትውከት "*አወከ" ስር ተመ.

ትውውቅ "አወቀ" ስር ተመ.

ትዛዝ "አዘዘ" ስር ተመ.

ትዝ

ትዝታ ስ 1.ትውስታ(የናፍቆት፥ የፍቅር፥...)። 2. የሙዚቃ ዜማ ቅኝት አይነት።

ትዝ አለ ግ ታወሰ፥ ታሰበ።

ትዝብት "ታዘበ" ስር ተመ.

ትያትር ስ በልብወለድ የድርሰት ዘዴ ተዘጋጅቶና ተቀናብሮ በመድረክ ላይ ለህዝብ የሚታይ የስነፅሁፍ ዘርፍ፤ ተውኔት።

ትያትር ቤት ስ ትያትር የሚታይበት አዳራሽ።

ትይዩ "እየ" ስር ተመ.

ትዳር ስ 1. ወንድና ሴት ባልና ሚስት ሆነው እንዲኖሩ የሚያስችላቸው፥ በቃልኪዳን የታሰረና ህጋዊ የሆነ ጥምረት፥ አንድነት። 2. የባልና የሚስት የአንድነት ኑሮ፤ ጋብቻ። 3. ቤት፥ ንብረት። 4. ባል ወይም ሚስት።

ባለትዳር ያገባ፥ ትዳር ያለው።

ትዳሩ ሞቀ ትዳሩ ተመቻቸ፥ ኑሮው ተሟላለት።

ትዳሩ ፈረሰ ከትዳር ጓደኛው ተለያየ።

ትዳር ያዘ/ያዘች ሚስት አገባ/ባል አገባች።

የትዳር ጓደኛ ስ ሚስት ወይም ባል።

ትጉህ "ተጋ" ስር ተመ.

ትጋት ዝ.ከ.

ትግ^1

ትግ አለ ግ አባራ፥ ቆመ (ዝናብ)።

ትግ^2

ትግ ትግ አለ ግ በቁጣ ወይም በንዴት ቶሉ ቶሉ ተናገረ፤ ግንፍል ግንፍል አለ።

ትግል "ታገለ" ስር ተመ.

ትጥቅ "ታጠቀ"ስር ተመ.

ትፉታም "ተፋ"ስር ተመ.

ትፋት ዝ.ከ.

ትፍ "እንትፍ" ን ተመ.

ትፍትፋት "ተፈተፈ" ስር ተመ.

ትፍትፍ ዝ.ከ.

ቶ የ"ተ" ፊደል ሳብእ ዘር።

ቶሎ ተውሳ.ግ ወዲያው፤ በፍጥነት፥ በአስቸኳይ።

ቶሎ በል ፍጠን፤ ቀልጠፍ በል።

ቶሎ ቶሎ ተው.ግ. 1. ወዲያው ወዲያው፤ እያከታተለ። *ቶሉ ቶሉ ያመዋል።* 2 .በፍጥነት። *ቶሉ ቶሉ ይራመዳል።*

ቶሎ ቶሎ አለ ግ ፈጠነ፥ ቸኮለ።

ቶረበ ግ አራርቆ በመውጋት በክር አያያዘ፤ ተራ ስፌት ሰፋ፤ ወሰወሰ፤ ሸደሸደ።

ቶራ ፈረስ ስ ጋማና ጭራ ያለው ባለሁለት ቀንድ የዱር እንስሳ(ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።

***ቶሰቶሰ**

ቶስቷሳ ቅ 1. አርፎ የማይቀመጥ ስነቧኳ። 2. ወሬኛ። 3. ፈሪ።

ተንቶሰቶሰ ግ 1. ወዲያ ወዲህ አለ፥ አውደለደለ። 2. በጣም ፈራ።

አቶሰቶሰ ግ ከሰር ከሰር ተከተለ፥ ወዲያ ወዲህ አለ (ለወሬ፥ ለስብቅ፥...)።

አቶስቷሽ ቅ ሰብቀኛ፥ አቶክቷኪ።

ቶታን ስ በመፃህፍት ጥራዝ ራስጌና ግርጌ ላይ እንደ ክፈፍ ወይም እንደጌጥ ተደርጎ የሚሰፋ ከብራና ወይም ከባህር አረብ ትልታይ የሚሰራ ጉንጉን።

ቶኒክ ስ ከጥራጥሬና ከፍራፍሬ የሚሰራ ውሃ የሚመስል የመጠጥ አይነት።

ቶንሲል "ቅምሆ" ን ተመ.

ቶፋ^1 ስ 1.እንደማሰሮ የሚያገለግልና ማሰሮ የሚመስል የሸክላ እቃ(ስእሉን የሸክላ እቃ ስር ተመ.)። 2. (ዘይ.) መልከ ጥፉ።

ቶፍቷፋ ቅ ወፍራምና ውስጡ ልል፤ ዶፈዶፍ።

ቶፋ^2 ስ የሌላን ሰው ስራ ወክሎ የሚሰራ (ለምሳሌ. ቄስን ወክሎ የሚቀድስ ወይም ባለርስትን ወክሎ የሚገብር)።

ቷ^1 የ"ተ" ፊደል ፍንፅቅ ዘር።

ቷ^2

ቷ አለ ግ 1. ጧ አለ፥ ፈነዳ፥ ተበጠሰ። 2. ፈጥኖ ወጣ፤ ፈሰሰ (ደም)። 3. ቦግ አለ፤ በራ።

ተንቷቷ ግ ተንጧጧ፥ ተከታታይ የፍንዳታ ድምፅ ሰጠ።

አንቷቷ ግ አንጧጧ፥ አከታትሎ ተኮሰ፥ አፈነዳ።

ቸ

ቸ ከ"ተ" ቀጥሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል (ግእዙ ሆሄ)::

ቸለሰ ግ 1. አብዝቶ ጨመረ:: 2. ከነበለ፥ አፈሰሰ፥ ደፋ (ፈሳሽን)::

ቸል

ቸልታ ስ 1. ምንቸገረኝነት፥ ለምንም ነገር ያለመጨነቅ:: 2. ተገቢ ምላሽ ለመስጠት ያለመፍጠን፣ ያለመፈለግ ስሜት:: 3. ልግመት::

በቸልታ ተው.ግ. በመናቅና በመተው፣ በምንቸገረኝነት፣ ምንም አይነት እርምጃ ባለመውሰድ:: *የተቃጣብንን ጥቃት በቸልታ ላናልፈውም::*

ቸልተኛ ቅ 1. ላንድን ጉዳይ ትኩረት ሰጥቶ የማይፈፅም፣ ግደየለሽ፣ ዳተኛ:: 2. ልግመኛ::

ቸልተኝነት ስ የምንቸገረኝነት፥ የግዴለሽነት ስሜት::

ቸል አለ (ችላ አለ) ግ ተወት አደረገ፣ ንቆ ተወ፣ ትኩረት ሳይሰጥ ቀረ፥ ለመፈፀም ወይም ለማከናወን ዳተኛ ሆነ::

ችላ ባይ ቅ ቸልተኛ፥ ግዴለሽነት የሚያበዛ::

ቸመቸመ ግ 1. አዶለዶመ፥ አደነዘ፥ ቸረቸመ:: 2. ደመደመ፥ አስተካከለ (አባጣ ጎባጣ የሆነውን):: 3. በመደዳ አሰለፈ፣ ገጠገጠ::

ቸምቻማ ቅ ዶልዷማ፥ ስለቱ የደነዘ::

ችምችም1. የተቸመቸመ፣ የተጠጋጋ:: *ችምችም ያለ መንደር::* 2. ተጠጋግቶና በቁመት ተስተካክሎ የበቀለ::

ተቸመቸመ ግ 1. በብዛት እጅብ ብሎ፥ ተጠጋግቶ በቀለ፥ ተቀመጠ፣... ተገጠገጠ:: 2. ዶለደመ::

ቸረ ግ ለገሰ፥ ሰጠ::

ቸር ቅ 1. ለጋስ፣ ደግ:: 2. በጎ፣ ደህና፣ መልካም:: *ቸር ያውልህ/ ቸር ያሰማህ::*

ቸር ወሬ የሚያሳዝን ነገር የሌለበት፣ ጥሩ የሆነ፣ የሚያስደስት ወሬ::

ቸርነት ስ ርህሩህነት፥ ለጋስነት፣ ደግነት::

ችሮታ ስ ስጦታ፥ ልግሳ::

*ቸረረ

ቸረር አለ (ቸር አለ) ግ እመር አለ፣ ተወርውሮ አለፈ፥ ዘለለ፥ ተስፈነጠረ::

ተንቻረረ ግ ተወረወረ፣ ተስፈነጠረ::

አንቻረረ ግ ወረወረ፥ አስፈነጠረ::

ቸረቸመ^{1} ግ አዶለዶመ፥ አደነዘ፥ ቸመቸመ::

ችርችም ቅ ስለቱ የደነዘ፣ ዱልዱም::

ቸረቸመ^{2} ግ በአፉ ሙሉ ቃመ (ጥሬን፣ ቆሎ፥...)::

ቸረቸረ ግ 1. እቃን ወይም ሸቀጥን በጅምላ ሳይሆን እየከፋፈለ በትንሽ በትንሹ ሸጠ፣ ሸቀጠ፣ ነገደ:: 2. ነዛ፥ አወራ:: *ጉራውን ይቸረችራል::*

ቸርቻሪ ስ እቃን ወይም ሸቀጥን በጅምላ ሳይሆን፥ በክፍልፋይ መልክ በትንሽ በትንሹ ለተጠቃሚ የሚሸጥ ነጋዴ::

ችርቻሪ ቅ ጅምላ ያልሆነ፣ በነጠላ ወይም በአነስተኛ መጠን የተገዛ(ሸቀጥ)::

ችርቻሮ ስ የሸቀጥ እቃ በጅምላ ሳይሆን በነጠላ ወይም በአነስተኛ መጠን ለተጠቃሚ የሚቀርብበት የንግድ አይነት::

ችርቻሮ ነጋዴ ስ ሸቀጥን በችርቻሮ የሚሸጥ ነጋዴ::

*ቸረቸፈ ግ አዶለዶመ፣ ቸረቸመ::

ችርችፍ ቅ ዱልዱም፣ ችርችም::

ተቸረቸፈ ግ ስለቱን አጣ፥ ዶለደመ::

ቸረፈፈ

ችርፍፍ አለ ግ ሞላ፣ ተንቸረፈፈ::

ተንቸረፈፈ ግ ሞላ አለ፥ ተንደረበበ፥ ስፍር ሊሆን ትንሽ ቀረው::

አንቸረፈፈ ግ ሞላ አደረገ፥ አንደረበበ::

ቸር "ቸረ" ስር ተመ.

ቸርቻሪ "ቸረቸረ" ስር ተመ.

ቸርነት "ቸረ"ስር ተመ.

*ቸሰሰ

ቸሰስ(ቸስ)አለ ግ 1. ውሃ በእሳት ወይም በጋለ ብረት ላይ ሲፈስ የሚሰጠውን አይነት ድምፅ ሰጠ:: 2. በረደ፣ ቀዘቀዘ (የጋለ ነገር በውሃ)::

ቸሰስ(ቸስ) አደረገ ግ 1. ቸስ የሚል ድምፅ እንዲሰጥ አደረገ:: 2. አበረደ፣ አቀዘቀዘ:: 3. አረካ (ውሃ ጥምን)::

ቸበቸበ ግ 1. በዱላ፣ በዘንግ ወቃ (እህልን በአውድማ ላይ):: 2. ሳይጎዳ በትንሹ መታ መታ አደረገ፣ ገረፈ:: 3. በብዛት ሸጠ፣ ሸቀጠ::

ቸብቸቦ ስ 1. ከአንገት በላይ ያለ አካል ከነቀንዳሳው ወይም ከነፀጉሩ:: 2. ፍጥነት ያለው የቤተክርስቲያን ወረብ ወይም የከበሮ ምት አይነት::

ቸብ አደረገ ግ1. በማይጎዳ ሁኔታ በቀስታ መታ አደረገ:: 2. ሸጠ::

ቸብ ቸብ አደረገ ግ 1.መታ መታ

አደረገ። 2. አጨበጨበ።

ተቸበቸበ ግ 1. ተወቃ። 2. ተገረፈ። 3. በብዛት ተሸጠ።

ቸነከረ ግ 1. በችንካር ወይም በምስማር መታ፥ ጠረቀ፥ አጣበቀ፥ ሰፋ፥ አያያዘ። 2. ቀረቀረ።

ችንካር ስ 1. ለመዝጊያነት እንዲያገለግሉ በተፈለፈሉ የሳንቃ ቀዳዳዎች ውስጥ የሚሰካ የእንጨት ትርቃር። 2.ብረት ነክ የሆኑ ነገሮችን ለማያያዝ የሚረዳ እንደ ሙጫ ያለ መጣብቅ። 3. ከብረታ ብረት የሚሰራ የድሮ የምስማር አይነት።

ተቸነከረ ግ 1. ተጣበቀ፥ ተሰፋ፥ ተያያዘ፥ ተወጋ (በምስማር ወይም በችንካር)። 2. ተቀረቀረ።

ቸነፈር ስ የተላላፊ በሽታ አይነት፥ ወረርሽኝ፥ ተስቦ ፥ እልቂት፥ መቅሰፍት።

ቸንቧ

ቸንቧ አለ ግ (ግዙፍ አካል) ከውሃ፥ ከባህር ውስጥ ተወርውሮ ሲገባ ቡጭ የሚል ድምፅ ተሰማ።

ቸንቧ ቸንቧ አለ ግ ውሃ ውስጥ ገብቶ ተንበጫረቀ።

ቸንቸ ስ ድድ። *በሎጢ ቸንቸን ብሎት ሄደ።*

ቸከ ግ 1. አደፈ፥ ቆሸሸ። 2. ሙዝዝ አለ፥ መነቸከ፥ አልለቅ፥ አልተው አለ።

ችክ ስ ጥርስ ላይ የሚጋገር እድፍ፥ ቆሻሻ፥ ልማም።

ችኮ ቅ ከያዘ የማይለቅ፥ መንቻካ፥ ሞዛዛ።

ችክ አለ ግ 1. በጣም ከመቆሸሹ የተነሳ ቢያጥቡት የማይለቅ ሆነ። 2. አልለቅ አለ፥ ቸከ። 3. አልተው አለ፥ ተሟዘዘ፥ ድርቅ አለ።

አቸከ ግ በጣም አሳደፈ፥ አቆሸሸ።

ቸከለ ግ ተከለ(ችካልን እመሬት ላይ)።

ችካል ስ መሬት ላይ የሚተከል ብረት፥ እንጨት፥ ካስማ።

ተቸከለ ግ መሬት ላይ ተተከለ።

ቸከቸከ ግ 1. መላልሶ ወጋ፥ ጨቀጨቀ። 2.ነቀሰ፥ ጠቀጠቀ። 3. አጠጋግቶ፥ አቀራርቦ ተከለ (አትክልትን)። 4. ነዘነዘ፥ ነተረከ፥ ዘበዘበ። 5. ጥቅጥቅ አድርጎ አብዝቶ ፃፈ።

ችክቻካ ቅ ነዝናዛ።

ተቸከቸከ ግ ጥቅጥቅ ያለ ሆነ (የአትክልት፥ የአፃፃፍ)።

***ቸከቸከ**

ተንቸከቸከ ግ ተንፈቀፈቀ፥ ተንተከተከ፥ በሰለ (ለምሳሌ. ወጥ)።

አንቸከቸከ ግ አንፈቀፈቀ፥ አንተከተከ፥ አበሰለ (ለምሳሌ ወጥን)።

ችክቻካ "ቸከቸከ"ስር ተመ.

ቸኮለ ግ 1.ተጣደፈ። 2. ፈጠነ።

ችኩል ቅ ርጋታ የሌለው፥ የሚጣደፍ፥ ረጋ ብሎ አስቦ የማይሰራ።

ችኮላ ስ ጥድፊያ።

ተቻኮለ ግ 1.ተጣደፈ። 2. ፈጠነ።

አቻኮለ ግ አጣደፈ።

አስቸኮለ ዝ.ከ.

አስቸኳይ ቅ አጣዳፊ፥ ጊዜ ወይም ፋታ የማይሰጥ።

የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ስ በጦርነት ወይም ከባድ አደጋ ምክንያት በሙሉ ሃገሪቱ ወይም በተወሰነ አካባቢ ጊዜያዊ ህግን ለመደንገግ የሚያስገድድ ሁኔታ።

ቸገረ ግ 1. ታጣ፥ ጠፋ። *ሙሼ ገንዘብ ቸገረ።* 2. ጨነቀ፥ ጠበበ። 3. ተሳነ፥ አቃተ።

ችጋር ስ እጦት፥ ረሃብ።

ችጋራም ቅ 1.(የን.አነ.) ያጣ የነጣ፥ ምንም የሌለው ደሃ። 2. (ስድብ) ገብጋባ፥ ስስታም፥ በልቶ የማይጠግብ።

ችግር ስ 1. እክል፥ እንቅፋት፥ ሳንካ። 2. መከራ፥ ጭንቅ፥ ፈተና። 3. አዳጋች ነገር። 4. ድህነት። 5. እጦት። *በመለዋወጫ ዕቃ ችግር ስራው አልተሰራም።*

ችግሩን ተወጣ ችግሩን ተቋቁሞ አሳለፈ።

ከችግር ወጣ ከችግር፥ ከጭንቅ ተላቀቀ፥ ተገላገለ።

ችግረኛ ቅ1. ያጣ፥ ርዳታ ፈላጊ። ስ 2. ደሃ።

ተቸገረ ግ 1. አጣ (የሚፈልገውን ነገር)። 2. ደሀየ። 3. መከራ፥ ጭንቅ ደረሰበት። 4. ተጨነቀ፥ ተጠበበ። 5 አቃተው፥ ተሳነው።

አስቸገረ ግ 1. አቃተ፥ አሸነፈ፥ አዳገተ። 2. አወከ። 3. አንድ ነገር እንዲደረግለት፥ እንዲሰራለት፥ እንዲፈፀምለት ጠየቀ፥ ወተወተ።

አስቸጋሪ ቅ 1. ለመስራት፥ ለመፈፀም፥ ወይም ለመገልገል የሚያዳግት፥ የሚያቅት። 2. አዋኪ፥ ጠባየ መጥፎ።

ቸገነ ግ የእፅዋትን ፍሬ ተቆፍሮ በተሰናዳ መሬት ላይ በመዝራት እንዲበቅል፥ እንዲፈላ አደረገ፥ ችግኝ አዘጋጀ።

ችግኝ ስ አዲስ የበቀለ የእፅዋት ፍል።

***ቸፈረረ**

ቸፍራራ ቅ ጨፍራራ።

ተንቸፈረረ ግ ደረቀ፥ ክችች አለ፥ ተንጨፈረረ።

አንቸፈረረ ግ አደረቀ፥ ክችች አደረገ፥

ኣንጨፈረረ::

ቸፈቸፈ ግ 1.ተፈተፈ፣ ብዙ ቦታ ላይ መላልሶ ወጋ፥ ጨቀጨቀ:: 2. ኣካፋ::

ቸፈቸፍ ስ የማያቋርጥ ካፊያ::

ቸፍቻፋ ቅ ጨቅጫቃ::

ችፍቻፌ ስ ቁርጥራጭ፥ ፍቅፋቂ (የእንጨት)::

ችፍ ችፍ አለ ግ ያለማቋረጥ የካፊያ ዝናብ ዘነበ::

ቸፈገ ግ ጠቀጠቀ፥ እጅብ አደረገ፥ ጨፈቀ::

ችፍግ ቅ እጅብ ያለ፥ ጭፍቅ::

ችፍግ አለ ግ አንድ ላይ እጅብ ብሎ በቀለ::

ቸፍራራ "*ቸፈረረ" ስር ተመ.

ቸፍቻፋ "ቸፈቸፈ" ስር ተመ.

ቹ የ"ቸ" ፊደል ካእብ ዘር::

ቺ የ"ቸ" ፊደል ሳልስ ዘር::

ቺንጊያ ስ ለሞተር ማዞሪያ የሚያገለግልና ከላስቲክ፥ ከሸራ፥... የተሰራ ክብ ጥብጣብ::

ቻ የ "ቸ" ፊደል ራብእ ዘር::

ቻለ ግ 1. አንድ ነገር ለማድረግ፣ ለማከናወን፥... አቅም አገኘ ወይም ብቁ ሆነ:: *ሃምሳ ኪሎ እቃ ለማንሳት ቻለ /ቤቱ አስር ሰው መያዝ ቻለ፡* 2. እውቀት፥ ችሎታ አገኘ፤ አወቀ:: *ቋንቋውን መናገር ቻለ / አማርኛ ይችላል / መኪና መንዳት ቻለ::* 3. መብት አገኘ፥ ኖረው:: *መስፈርቱን የሚያሟሉት በሙሉ መምረጥና መመረጥ ይችላሉ::* 4. በቂ ሆነ:: *ገንዘቡ ሙሉ ልብስ መግዛት ቻለ፡* 5. ከፈለ፥ ሸፈነ(ወጪን):: *ዩኒቨርሲቲው መኝታና ምግብህን ይችላል::* 6. ታገሰ:: 7. ተቋቋመ:: *ብርዱን ላልቻልከትም /ሙቀው ላደጋ ይችላል::*

ቻይ ቅ 1. ታጋሽ:: 2.አደጋ ወይም አስቸጋሪ ሁኔታን የሚቋቋም::

ችሎት ስ የዳኝነት ስራ የሚካሄድበት ቦታ፥ ሸንጎ::

ችሎት አስቻለ ዳኝነት ለማየት ተሰየመ::

ችሎታ ስ 1.አቅም:: 2. አንድን ነገር የማካሄድ፣ የመስራት እውቀት:: 3. ስልጣን::

ተቻለ ግ አንድን ነገር ለማድረግ፥ ለማከናወን፥...አቅም፥ መብት፥ ፈቃድ፥...ተገኘ::

በተቻለ መጠን የአቅምን ያህል በመሞከር ወይም እንደምንም:: *በተቻለ መጠን ነገ ለመመለስ ሞክር::*

አልተቻለም 1. አዳጋች ሆነ፥ አቃተ:: 2. አልተሳካም::

የተቻለው ነው ሃብታም ነው::

የተቻለውን ያህል አቅም የፈቀደውን ያህል::

ይቻላል 1. (ማድረግ፥ ማካሄድ፥ መሆን፥...) የተፈቀደ ነው፣ ክልክል የለውም:: 2. (ለማድረግ፥ ለማካሄድ፥ ለመሆን፥...) እድሉ፥ አቅሙ አለ:: *ከዚያ በሗላ መሃንዲስ ለመሆን ይቻላል::*

አይቻልም 1. በጣም ሃይለኛ፥ አስቸጋሪ ነው፤ ሊቋቋሙት ያዳግታል:: 2. አይሆንም፥ አይደረግም፥ አይፈቀድም::

ተቻቻለ ግ 1. (ክፍያ፥ ወጪ፥ ኪሳራ፥ እዳ፥...) ተጣጣ፥ ተብቃቃ፥ ተካከሰ:: 2. አንዱ ሌላውን ታግሶ፥ እርስ በርስ ተከባብሮ፥ ተፈቃቅዶ አብሮ ኖረ::

አቻቻለ ግ አጣጣ፥ አብቃቃ (እዳን፥ ክፍያን)::

አስቻለ ግ 1. አበቃ፥ ብቁ አደረገ፥ ረዳ:: 2. ትእግስት ሰጠ:: 3. ችሎት ላይ ተቀመጠ፥ ተሰየመ (ለመዳኘት ወይም በዳኝነት ለመመልከት)::



ቻርኔላ

ቻርኔላ ስ ተከፋች በሆነ ኮት፥ ቦርሳ፥ ሸንጣ፥...ላይ የሚሰፋና እርስ በርሱ ሊቆላለፍ የሚችል መዝጊያና መክፈቻ፤ ዚፕ እየተባለም ይጠራል::

ቻቻ

ቻቻታ ስ ጫጫታ፥ ውካታ::

ተንቻቻ ግ ተንጫጫ::

አንቻቻ ግ አንጫጫ::

ቻይ "ቻለ" ስር ተመ.

ቼ^{1} የ"ቸ" ፊደል ሃምስ ዘር::

ቼ^{2} ፈረስ እንዲሄድ፥ እንዲሮጥ፥ እንዲጋልብ ለማድረግ የሚባል::

ቼቼ ስ ልዘልህ ወይም ና ታዘል (ፈረስ ልሁንልህ እንደ ማለት) ለማለት ለህፃን የሚነገር ቃል::

ቼቼ አለ ግ በጀርባ ተሸከመ፥ አዘለ (ልጅን)::

ቼዝ ስ ሰንጠረዥ ጨዋታ::

ች የ"ቸ" ፊደል ሳድስ ዘር::

-ች በግስ ላይ በስተመድረሻ እየተቀጠለ ሶስተኛ መደብ አንስታይ ጾታን የሚያመለክት ምእላድ:: (ለምሳሌ ወሰደች፥ ትማራለች...)::

ችላ ባይ "ቸል"ስር ተመ.

ችሎታ "ቻለ"ስር ተመ.

ችሎት ዝ.ከ.

ችምችም "ቸመቸመ" ስር ተመ.

ችርቻሪ "ቸረቸረ" ስር ተመ.

ችርቻሮ ዝ.ከ.

ችርችም "ቸረቸመ^{1}"ስር ተመ.

ችርችፍ "ቸረቸፈ" ስር ተመ.

ችሮታ **"ቸረ"** ስር ተመ.

ችብሃ ስ ውትት የሚወጣውና ለምለምነት የማይለየው እንደሾላ ያለ ዛፍ።

ችቦ ስ 1. በመብራትነት የሚያገለግል ባንድነት የታሰረ ጭራሮ፥ ሽግ ወይም ጸቦት። 2. ለቡሄ ወይም ለእንቁጣጣሽ ዋዜማ እንዲሁም የደመራ እለት (ለመስቀል ዋዜማ) የሚበራ ባንድነት ከታሰረ ጭራሮ የሚዘጋጅ የበአል መብራት (ችቦ የሚበራበት እለት እንደየአካባቢው ሊለያይም ይችላል)።

ችንካር **"ቸነከረ"** ስር ተመ.

ችኩል **"ቸኮለ"** ስር ተመ.

ችካል **"ቸከለ"** ስር ተመ.

ችክ¹

ችክ ችክ አለ ግ ያለማቋረጥ የካፊያ ዝናብ ዘነበ።

ችክ² ግ **"ቸከ"** ስር ተመ.

ችኮ ዝ.ከ.

ችኮላ **"ቸኮለ"** ስር ተመ.

ችጋራም **"ቸገረ"** ስር ተመ.

ችጋር ዝ.ከ.

ችግ¹ በግን ለማባረር፥ ሂድ ለማለት የሚባል።

ችግ አለ ግ ሂድ አለ (በግን)።

ችግ²

ችግ አለ ግ ተንገረገበ (ጥሬ)።

ችግ አደረገ ግ አንገረገበ (ጥሬን)።

ችግ³

ችግ አለ ግ እጅብ ብሎ ወጣ፤ በቀለ (እፅዋት)።

ችግረኛ **"ቸገረ"** ስር ተመ.

ችግር ዝ.ከ.

ችግኝ **"ቸገኘ"** ስር ተመ.

ችፌ ስ አብዛኛውን ጊዜ በእጅና በእግር ላይ ሽፍ ብሎ የሚወጣ፤ የሚያሳክክና እዥ የሚይዝ የቁስል አይነት።

ችፍ

ችፍታ ስ ሽፍ ብሎ በሰውነት ላይ የሚወጣ እንደ እከክ ያለ ነገር።

ችፍ አለ ግ በሰውነት ላይ ሽፍ ብሎ ወጣ (እከክ፥ ሽፍታ)።

ችፍርግ ስ ቁመቱ በጣም አጭር ከመሆኑ የተነሳ ብዛት ያላቸው ቅርንጫፎቹ መሬት ላይ ተኝተው የሚታዩ፤ ጠንካራ ሆኖ ውልግድግድ ያለ ግንድ ያለው አነስተኛ የእፅዋት አይነት።

ችፍታ **"ችፍ"** ስር ተመ.

ችፍቻፊ **"ቸፈቸፈ"** ስር ተመ.

ችፍግ **"ቸፈገ"** ስር ተመ.

ቾ የ"ቸ" ፊደል ሳብእ ዘር።

ቾክ ስ ለስላሳና ነጭ ከሆነ ድንጋይ የሚሰራ፤ በጥቁር ሰሌዳ ላይ ለመፃፍ የሚያገለግል ብዙ ጊዜ ቀለሙ ነጭ የሆነ የፅህፈት መሳሪያ፤ "ጠመኔ" እየተባለም ይጠራል።

ቿ የ"ቸ" ፊደል ፍንፅቅ ዘር።

ን

ን (በዚህ መዝገብ) ቃላት ፊደል ተራ መሰረት ከ"ቸ" ፊደል ዘር ቀጥሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል (ግእዙ ሆሄ)።

ንሃሴ (ናሴ) ስ ከሃምሌ ቀጥሎ የሚመጣ የአመቱ አስራ ሁለተኛ ወር ስም።

ንሃስ(ንሃስ፡ናስ) ስ ቀለሙ ወደ ቢጫ የሚጠጋ፡ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል፡ የቆርቆሮና የመዳብ ቅይጥ የሆነ የማእድን አይነት።

ነሁላላ "**ነሆለለ**" ስር ተመ.

ነህ (አፍ. "**አይደለህም**") "**ነው**"ን ተመ.

ነሆለለ ግ ሞኘ፡ ቂል፡ ፈዛዛ ሆነ፡ ጀለ።

ነሁላላ (ነሆለል) ቅ ሞኝ፡ ቂል፡ ፈዛዛ፡ጅል።

ተነሃለለ ግ ነሆለለ፡ ቄለ፡ ተጃጃለ።

ነረተ¹ ግ ከፍኛ መታ፡ ጠለዘ፡ ደበደበ።

ነረተ² ግ 1. ነፋ፡ ቀበተተ(ሆድን) 2. አወፈረ፡ አደነደነ።

ናረት ስ ጸሁላ፡ ትልቅ እቁማጸ፡ ጭልጊ።

ናረት ሆድ ቅ (በዘይ.)ሆዱ ትልቅ የሆነ፡ በርጫም።

***ነረነረ**

ነርነርቱ ቅ አነጥናጭ፡ አደዝዳዥ፡ ወይሳ።

አነረነረ ግ አደዘደዘ፡ አነጠነጠ፡ ወደሰ።

ነርስ ስ በሆስፒታል ውስጥ ሃኪሙን በስራ ለመርዳትና የህመምተኞችን ጤና ለመከታተል የሰለጠነ ወይም የሰለጠነች የህክምና ባለሙያ።

ነሰረ ግ ከአፍንጫ ውስጥ ደም ወጣ፡ ፈሰሰ (በህመም)።

ነስሮታል 1. ነስር አጥቶታል። 2. በዝቶበታል። *ማጡ ቅቤ ነስሮታል።*

እስኪነስረው እስኪበቃው፡ እስኪያቅለሸልሸው። *እስኪነስረው ልክ ልኩን ነገረው።*

ነስር ስ ከአፍንጫ ውስጥ ደም እንዲፈስ የሚያደርግ ህመም፡ የሚፈሰው ደምም ነስር ይባላል።

አነሰረ ግ ከአፍንጫ ውስጥ ደም ወጣ፡ ፈሰሰ (በህመም ምክንያት)።

አይነሰረውም ምንም ገንዘብ አይሰጥም፡ ስስታም ነው።

አስነሰረ ግ አደማ (አፍንጫን)።

ነሰነሰ ግ 1. ጎዘጎዘ፡ በተነ (ሳርን)። 2.አንቀሳቀሰ፡ ወዘወዘ (ጭራን)። 3. በቁጣ ፀጉሩን አቆመ (ለምሳሌ. ድመት)። 4. በተነ። *ቁስሉ ላይ መድሃኒት ነሰነሰበት።* 5. (ዘይ.) ሀ. ነዛ። *ጉራውን ነሰነሰ።* ለ. ያለማባባት አባከነ፡ በተነ፡ አጠፋ (ገንዘብን)።

መነሳንስ ስ በጭራ መልክ የሚሰራና እንደጭራ ያለ የሃር ጎፍላ ወይም የሃር ፈትል።

ተነሰነሰ ግ ተሰራጨ፡ ተዘራ። *በሽታ በአገሩ ላይ ተነሰነሰ።*

ነሲብ ስ ያልተለካ፡ ያልተመዘነ የግምት አስተያየት።

በነሲብ በግምት፡ ሳይለኩ፡ ሳይመዝኑ። *እህሉን የገዛሁት በሚዛን ሳይሆን በነሲብ ነው።*

መነሳንስ

ነሳ¹ ከለከለ፡ ሳይሰጥ ቀረ። *ሲጋ ሰጥተው ሊነሱ ነው።*

ተነሳ(ተነሳው) ግ አጣ፡ ራቀው፡ ተከለከለ። ረድኤት ነሳው።

ነሳ² ግ ወሰደ። *ከስጋዋ ስጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ ሰው ሆነ።*

ነሳ³ ግ "**እጅ**" ስር "**እጅ ነሳ**"ን ተመ.

መንስኤ ስ ሰበብ፡ ምክንያት መነሻ።

ተነሳ ግ 1. ብድግ አለ፡ ቆመ። 2. ተላወሰ፡ ተንቀሳቀሰ፡ ነቃ (ለምሳሌ ከእንቅልፍ)። 3. ተንቀሳቀሰ፡ ጉዞ ጀመረ። *ዛሬ ከጧቱ በሁለት ሰአት ተነሳ።* 4. ተጀመረ፡ መጣ። *ጦርነት ተነሳ/ጠቡ በምን ተነሳ።* 5. መጣ፡ ገባ። *በሽታ ተነሳ።* 6. ተሻለው፡ ዳነ። *ታሞ የነበረው ተነሳ።* 7. ነፍስ ዘራ፡ ከሞት ወደ ህይወት ተመለሰ። *አልአዛር ከሞተ ከአራት ቀን በኋላ ከመቃብር ተነሳ።* 8. በነ፡ ከፍ አለ። *ሊጡ ተነሳ።* 9. ተሸጠ፡ ገዢ አገኘ። *ሸቀጡ ተነሳ።* 10. ሃብት አገኘ፡ ከበረ፡ ገነነ። *የተነሳው በቆዳ ንግድ ነው።* 11. ተወሳ፡ ተጠራ፡ ተነገረ። *በዚህ ጉዳይ ስሙ ተነስቶም አያውቅም።* 12. ተቀነሰ፡ ተከፈለ፡ ተወሰደ። *ከአስሩ ላይ አራቱ ስለተነሳለት ቀረው ስድስት ብቻ ነው።* 13. ተሻረ፡ ተሰረዘ፡ ተለቀቀ። *ስለት ለሰረው ተነሳ።* 14. በልቡ አሰበ፡ ወሰነ፡ ቆረጠ። *ልቡ ተነሳቷልና ከመሄድ አይቀርም።* 15. ተቀሰቀሰ፡ አበረ፡ በአንድ አላማ ተሰለፈ። *ህዝቡ ተነሳ።* 16. ተወገደ። *መሰናክሉ ወይም እንቅፋቱ ተነሳ።*

መነሻ ስ የአንድ ነገር ወይም ድርጊት መጀመሪያ (ቦታ፡ ጊዜ፡ ምክንያት)።

መነሸ ስ 1. መነሻ፡ ሰበብ፡ ምክንያት። 2. ለጠበቃ ወይም ለስራ ተዋዋይ መጀመሪያ ላይ የሚከፈል የገንዘብ መጠን። 3. በሙታን ስም ተዘጋጅቶ ለካህናት ከሚቀርብ ፀበል ፀዲቅ ላይ ተቀንሶ ለካህናቱ አለቆች የሚሰጥ መጠነኛ ምግብና መጠጥ።

ተነሳሳ ግ ተነቃቃ፡ ተደፋፈረ፡ ተገፋፋ (አንድ ነገር ለማድረግ)።

አነሳ ግ 1. ከፍ፡ ብድግ አደረገ። 2. ጀመረ፡ አጫረ። *ጦርነት አነሳ*። 3. አከበረ፡ አበለፀገ፡ አላቀ። እሱን ያነሳው የጨው ንግድ ነው። 4. አወሳ፡ አስታወሰ። *ያለፈውን እያነሳ ተጫወተ*። 5. ወሰደ። *እዚህ የነበረውን እቃ ማን አነሳው?* 6. ተወ፡ ሰረዘ። *ላቀረበት የነበረውን የተቃውሞ ሃሳብ አንስቷል*። 7. በብዛት ወሰደ፡ ፈጀ። *ዱቄቱ ውሃ ያነሳል*። 8. አጠቃሎ ያዘ፡ ቻለ። *በሶስት ማድጋዎች የነበረውን ድፍድፍ አንድ በርሜል አነሳው*። 9. አምኖ ተቀበለ። *ያባቱን እዳ አነሳ*። 10. ተከተለ፡ አጠና፡ ያዘ፡ ተማረ። *ልጅየው ያባቱን ሙያ አንስቷል*። 11.(ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) የሚቀጥለው ጊዜ ተረኛ በመሆኑ የእለቱ ተረኛ መሪ የሚያዜመውን እየተቀበለ አዜመ።

ንሳ በል፡ እባክህ። *ንሳ ያንን እቃ አቀብለኝ / ንሳ ተቀበል*።

አንሺ ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ከእለቱ ተረኛ የዜማ መሪ ቀጥሎ ተረኛነቱን የሚረከብ (መዘምር፡ ደብተራ)።

አነሳሳ ግ1. አበረታታ፡ አደፋፈረ፡ ገፋፋ። 2. ቀሰቀሰ፡ አሳደመ።

አነሳሽ ቅ ቀስቃሽ፡ አሳዳሚ።

አስነሳ ግ እንዲነሳ አደረገ።

ነስር "ነሰረ" ስር ተመ.

ነሸጠ ግ በል በል፡ አድርግ አድርግ የሚል ስሜት ተሰማ፡ ገፋፋ፡ አነሳሳ።

ነሸጥ አደረገ ግ ነሸጠ።

ንሽጥ አደረገ ዝ.ከ.

ነሽ (አፍ. **አይደለሽም**) "ነው" ን ተመ.

ነቀለ ግ 1. መዘዘ፡ መነገለ። 2. አወለቀ፡ ለየ። 3. አባረረ፡ አስወገደ(ከርስት)። 4. ሰረዘ፡ ፋቀ (ከመዝገብ)። 5. አጠፋ (በሽታን)። 6. ጥርግ ብሎ ሄደ። *ሰራዊቱ ካደረበት ቦታ በሌት ነቅሎ ሄደ*። 7. (ዘይ.) አረቆተ፡ አደበየ። *ብድር ወጪው / ነቀለኝ*።

ነቀሳ ስ እንግጫ የሚነቀልበት የእንቁጣጣሽ ዋዜማ።

ነቀል ተከል ቅ በአንድ በተወሰነ ቦታ በቋሚ የማይኖር፡ እንደዘላን ጎጆ ወይም ቋሚ ቦታ የሌለው።

ነቃሳ ቅ 1. ሲራመድ ድፍት ድፍት ያለ የሚመስልና ፈጠን ያለ አረማመድ ያለው፡ ቀትረ ቀላል (ሰው)። 2. (ስድብ) ጥላቢስ።

ነቃይ ተካይ ስ የመሻር፡ የመሾም፡ ከርስት ላይ የማባረር፡... ስልጣን ያለው ሹም።

ንቃይ(ንቅል) ስ አገልግሎት ላይ እንዲውል ተደርጎ ከቆየ በኋላ ፈርሶ ወይም ከነበረበት ተነስቶ ለሌላ ተግባር ሊውል የሚችል (የአጥር እንጨት፡ የቤት ክዳን ቆርቆሮ፡...)።

ነቀልቃል "*ቀለቀለ" ስር ተመ.

***ነቀረ**

ንቃሬ (እንቃሬ) ስ ጭላጭ፡ ሙጣጭ (ፈሳሽ ለሆነ ነገር)።

አነቀረ ግ ሙጥጥ አድርጎ ወሰደ፡ ጨለጠ (ፈሳሽን ከመያዣው ውስጥ)።

አንቅሮ ተፋ ፈፅሞ ጠላ፡ ተወ፡ የነበረውን ግንኙነት አቋረጠ።

ነቀርሳ ስ ብዙውን ጊዜ በአንገት፡ በጡት፡ በደረት፡...አካባቢ የሚፈጠርና በቀላሉ የማይሽር ወይም ጭራሹኑ ሊሽር የማይችል ጠንቀኛ የቁስል በሽታ አይነት።

ነቀርሳ ሆነበት 1. ሲጀምር ቀላል የነበረው የቁስል ህመም ውሎ አድሮ ወደ ነቀርሳ ተለወጠበት። 2. (ዘይ.) የማያገላግለውና የማይላቀቀው ችግር ሆነበት (ለነገር)።

ነቀሰ ግ 1. የጥላሸት ቀለም በተቀባ የመርፌ ወይም የእሾህ ጫፍ ገላን(ድድን፡ አንገትን፡...) ደጋግሞ በመውጋት ወይም በመጠቅጠቅ የተወጋው ገላ ጠቋራ እንዲሆን አደረገ፡ በንቅሳት አስጌጠ፡ ወቀረ። 2. ከወርቅ፡ ከብር፡... በሚሰራ ጌጥ ላይ የተለያየ ቅርፅ በመንደፍ ጌጡን አስዋበ። 3. የተፈተለተለውን፡ የተቆጣጠረውን የራስ ፀጉር በሚዶ አበጠረ ወይም ከፈከፈ። 4. ቆሻሻን ወይም ጉድፍን ከልብስ ወይም ከጥጥ ላይ አነሳ። 5. ነቀለ፡ መነገለ (እሾህን ከእግር፡ ፀጉርን ከአይን ቆብ ዳር ላይ)።

መንቀሻ ስ 1. ለንቅሳት ስራ የሚያገለግል መርፌ ወይም እሾህ። 2. ማበጠሪያ፡ ሚዶ።

በንቂስ አንድም ሳይቀር፡ በሙሉ። *ህዝቡ በንቂስ ወጣ*።

ንቃሽ ስ ከልብስ፡ ከጥጥ፡... ላይ የተለቀመ ጉድፍ ወይም ቆሻሻ የበዛበት ጥጥ ወይም በርበሬ።

ንቅሳት ስ ጥላሸትን በውሃ በጥብጦ በመርፌ ወይም በእሾህ ጫፍ እየጠቀሱ ገላን (ድድን፡ አንገትን፡...) ደጋግሞ በመጠቅጠቅ የሚሰራ የሰውነት ላይ ጌጥ፡ ውቅራት።

ንቅስ ስ 1. ንቅሳት። 2. ለጌጥ፡ ለውበት ተብሎ እንደ ሽክና፡ መስቀል፡ ዋንጫ፡... ባሉ ቁሳቁሶች አካል ላይ የሚሰራ ቅርፅ፡ ሽልማት።

ነቀሰ^{2} ግ መሰከረ፣ እውነትን ከሐሰት ለይቶ ተናገረ።

ንቃሽ ስ ምስክር፣ እማኝ።

ነቀሰ^{3} ግ ቀነሰ፣ ወረደ (ዋጋ)።

ንቃሽ ቅ የዋጋ ቅናሽ።

በንቃሽ በቅናሽ።

***ነቀሸ**

አነቀሸ ግ ሰበረ፣ አነከተ።

እንቅሽ አለ ግ ተሰበረ፣ ነከተ።

እንቅሽ አደረገ ግ ሰበረ፣ አነከተ።

ነቀነቀ ግ 1. ወዘወዘ፣ ናጠ፣ ጎነተለ፣ ገሸመ። 2. ቀሰቀሰ፣ አነሳሳ። *ፕሮፖጋንዳው ህዝቡን ነቀነቀው።*

ንቅናቄ ስ 1. ቅስቃሴ፣ ውዝዋዜ። 2. እንቅስቃሴ (የአመፅ፣ የተቃውሞ)።

ንቅንቅ ብሎ ወጣ ግልብጥ ብሎ በብዛት ወጣ። *ህዝቡ ንቅንቅ ብሎ ወጣ።*

ንቅንቅ አይልም አይበገርም፣ አይሞከርም፣ ፍንክች አይልም።

ተነቀነቀብኝ - ተገቢ ካልሆነ አነጋገር ጋር የትእቢት፣ የንቀትና የቁጣ አካላዊ እንቅስቃሴ አሳየኝ፣ ተረገረገብኝ።

ተነቃነቀ ግ 1. ተወዘወዘ። 2. ተንቀሳቀሰ። 3. ተነሳሳ፣ ተቀሰቀሰ።

ተነቃናቂ ቅ ተዘዋዋሪ፣ ተንቀሳቃሽ።

አነቃነቀ ግ 1. አወዘወዘ፣ አንቀሳቀሰ። 2. አነሳሳ።

ነቀዘ ግ 1. በነቀዝ ተበላ፣ ተበላሸ። 2. ነቀዝ አፈራ፣ ፈጠረ።

ነቀዝ ስ 1. ሙቀት ባለበት አካባቢ የሚፈጠርና አንዳንድ የእህልና የእንጨት አይነቶችን ውስጣዊ አካል በመቦርቦርና በመብላት ለብልሽት የሚዳርግ አነስተኛ የተባይ አይነት። 2. (ስድብ፣ ዘይ.) ብዙ የሚበላና በልቶም የማይጠረቃ (ሰው)።

ነቀፈ ግ 1. ተቸ፣ ተቃወመ። 2. አንኳሰሰ፣ አጥላላ፣ እንከን አወጣ።

ነቀፋ ስ 1. ትችት፣ ቅዋሜ። 2. እንከን፣ ነውር ማውጣት።

ነቀፌታ ዝ.ከ.

ነቃፊ ቅ 1. ተቺ፣ ተቃዋሚ። 2. አቃቂር፣ እንከን አውጪ።

***ነቀፈ**

አነቀፈ ግ 1. አደናቀፈ፣ አሰናከለ፣ መታ (እንቅፋት እግርን)። 2. ጣልቃ በመግባት ችግር ፈጠረ፣ መሰናክል ሆነ።

እንቅፋት ስ 1. ሲራመዱ እግርን የሚያደናቅፍ፣ የሚያሰናክል እንደ ድንጋይ፣ ጉቶ፣... ያለ ነገር። 2. ሳይታሰብ የሚያጋጥምና አንድን ጤናማ ሂደት የሚያውክ ችግር፣ መሰናክል።

እንቅፋት አነደደው እንቅፋት እግሩን መታው።

ነቀፋ "ነቀፈ" ስር ተመ.

ነቀፌታ ዝ.ከ.

ነቁጥ "*ነቆጠ" ስር ተመ.

ነቃ^{1} ግ 1. እንቅልፉን ጨረሰ፣ ከእንቅልፉ ተነሳ። 2. ባነነ፣ ከእንቅልፉ ተቀሰቀሰ። 3. ንቁ፣ ትጉህ፣ ቀልጣፋ ሆነ። 4. ጠረጠረ። 5. አወቀ፣ ተረዳ፣ ፈጥኖ ተገነዘበ።

ንቁ ቅ 1. እንቅልፍ የማያሸንፈው፣ ባስፈላጊው ጊዜ መነሳት የሚችል። 2. ትጉህ፣ ቀልጣፋ፣ ሎሊ።

ንቃት ስ 1. ትጋት፣ ቅልጥፍና። 2. አርቆ የማስተዋል፣ ሁኔታዎችን ፈጥኖ የመረዳት ችሎታ። 3. ከፖለቲካዊ ትምህርት የሚገኝ እውቀት፣ ግንዛቤ።

ንቃተህሊና ስ የተግባራዊና የነባራዊ ሁኔታ ነፀብራቅ ውጤት የሆነ የሰው ልጅ የአእምሮ ግንዛቤ፣ አስተሳሰብ፣ እውቀት።

አነቃ ግ የፖለቲካ ትምህርት አስተማረ፣ ቀሰቀሰ።

አንቂ ስ የፖለቲካ ትምህርት ለህዝብ የሚሰጥ፣ ቀስቃሽ።

አነቃቃ ግ አበረታታ፣ ገፋፋ፣ ጎተጎተ፣ ቀሰቀሰ።

ማንቂያ ስ ማበረታቻ።

ነቃ^{2} ግ ተሰነጠቀ፣ ተተረተረ።

ንቃቃት ስ ስንጥቃት፣ ትርትራት (የመሬት፣ የእግር፣...)።

ንቃቃታም ቅ (ስድብ) እግሩ ላይ ንቃቃት ያለበት፣ በንቃቃት የተጎዳ (ሰው)።

ነቃላ "ነቀለ" ስር ተመ.

ነቃሽ "ነቀሰ^{2}" ስር ተመ.

ነቃፊ "ነቀፈ" ስር ተመ.

***ነቆረ**

መንቆር ስ 1. የወፍ፣ የአሞራ፣ የዶሮ አፍ። 2. ባላ ያለው ረዘም ያለ እንጨት። 3. እንደ እግር ብረት ሆኖ ለማሰረያነት የሚያገለግል ቀዳዳ ወይም ብስ ያለው ግንድ።

ንቋራ ቅ አንድ አይኑ የጠፋ።

ተናቆረ ግ 1. አንዱ ከሌላው ጋር ተነካከሰ (ዶሮ)። 2. አንዱ ከሌላው ጋር ተጣላ፣ ተጣመደ፣ ተያያዘ።

አንቆረ ግ1. ወጋ፥ ደነቆለ፥ ጠነቆለ (ዓይንን)። 2. ጫረ፥ ቆሰቆሰ (ነገርን)።

አናቆረ ግ አጣላ፥ አናከሰ።

***ነቆጠ**

ነቁጥ ስ በቃል፥ በሃረግና በአረፍተ ነገር መጨረሻ ላይ የሚደረግ ነጥብ።

አነቆጠ ግ ነጥብ አደረገ፥ አስቀመጠ።

ነቋራ "***ነቆረ**" ስር ተመ.

ነበልባል "***በለበለ**" ስር ተመ.

ነበረ(ነበር) ግ የ 'ነው' እና የ "አለ" ሃላፊ ጊዜ ግስ። *ዛሬ ፀሃይ ነው ትናንት ግን ዝናም ነበረ /ለለች እንጂ ነበረች ኣይጠቀምም።*

ለነበር ለውግ፥ ለዝና፥ ለማስታወሻ፥ ለታሪክ። *ለነበር ይጠቅማልና ታሪካችን በወጉ ተፅፎ ቢቀመጥ ኣይከፋም።*

ነበርኩ ባይ እንዲህ ነበርኩ እያለ በማውራት የሚኩራራ ጉረኛ።

ነባሪ ስ ምስክር፥ እማኝ።

ነባራዊ ቅ ተጨባጭ የሆነ (ነገር)።

ነባር ቅ የኖረ፥ የቆየ። *ሰውየው በዚህ ቦታ ነባር ናቸው።*

ነበረረ ግ 1. ቁለ፥ ነሆለለ። 2. ተንገባረረ።

ነበረር(ነብራራ) ቅ 1 ነሁላላ። 2. ገብራራ።

ተነባረረ ግ ነበረረ።

አነባረረ ግ 1. አቁለ፥ አነሆለለ። 2. አንገባረረ።

***ነበረበረ**

ንብርብር (ንብብር) ቅ ድርብርብ (አንዱ በሌላው ላይ ተደርቦ መገኘት)።

ንብርብር አለ ግ ተነባበረ።

ተነባበረ ግ 1. ተደራረበ፥ አንዱ በሌላው ላይ ሆነ። 2. ተጋገዘ፥ ተረዳዳ።

አነባበረ ግ አንዱን በሌላው ላይ አደረገ፥ አደራረበ።

አነባበሮ ስ በሰሉ የሆነን እንጀራ ምጣድ ላይ ከተሰፋና ገና ካልበሰለ ሊጥ (እንጀራ) ላይ በመደረብና አብሮ በማብሰል የሚዘጋጅ ወፍራምና ድርብርብ እንጀራ።

ነበር "**ነበረ**" ን ተመ.

ነበበ ግ 1. ታወቀ፥ ከበረ፥ ገነነ። 2. በሃይል ጮሀ፥ ጩሀት አስተጋባ፥ ከፍቶ ተሰማ (የከበሮ፥ የመረዋ)።

***ነበበ**

ምንባብ ስ 1. አጠር ያለና ለንባብ ማስተማሪያ የተዘጋጀ ፅሁፍ። 2. መፅሃፍ፥ መጣጥፍ፥ ፅሁፍ።

ንባብ ስ 1. በፅሁፍ ላይ የሰፈረን ነገር በአንደበት ወይም በድምፅ አማካይነት ጮክ አድርጎ የማነብነብ፥ የመናገር፥ የማሰማት ድርጊት። 2. በቤተክህነት ትምህርት ቤት ከውርድ ንባብ ቀጥሎ የሚሰጥ የአነባበብን ተራትና ፍጥነት የሚመለከት ትምህርት።

ንባብ ቤት ስ (ቤ.ክህ.) ከፊደል እስከ ዳዊት ያለውን ትምህርት የሚማሩበት ትምህርት ቤት።

ተነበበ ግ 1. በንባብ ተባለ፥ ተነገረ (ፅሁፍ ላይ የሰፈረው ነገር)። 2. የሚታይና የሚነበብ ወይም ሊነበብ የሚችል ሆነ። *ፅሁፉ ኣይነበብም።*

ተነባቢ ቅ 1. አጣጣሉ ግልፅና ጥሩ ሆኖ የተፃፈና ለአንባቢ የማያስቸግር (ፅሁፍ)። 2. ተወዳጅ ፅሁፍ በመሆኑ ብዙዎች የሚያነቡት።

ተናበበ ግ1. ተመሳከረ፥ ተያየ (ዋናው ፅሁፍ ከቅጂው ጋር አንድ አይነት ስለመሆኑ)። 2. አንዱ የሌላውን ሃሳብ ተረዳ፥ በዚህም መንገድ ተግባባ፥ ተዋወቀ።

ተናባቢ ስ 1. ለየብቻቸው ሳይሆን እንደ አንድ ቃል ተደርገውና በአንድነት ተጠቅለው የሚነገሩ ጥምር ቃላት (ለምሳሌ ቤተመንግስት፥ ርእሰብሄር፥...)። 2.(ስነል.) ከአፍ ውስጥ የሚወጣው አየር ሲቆም ወይም ሲታገድና ሲጋጭ የሚፈጠር እንደ (ብ፥ረ፥ክ፥... ያሉና አናባቢ ያልሆነ ድምፅ።

አነበበ ግ በፅሁፍ ላይ የሰፈረን ነገር ድምፅ እየሰማ በአንደበቱ አለ፥ ተናገረው ወይም ድምፅ ሳይሰማ በአእምሮው ዘለቀው።

አንባቢ ቅ 1. የማንበብ ችሎታ ያለው። 2. አዘውትሮ መፃህፍትን ማንበብ የሚወድ። 3.ስራው ጮክ ብሎ ማንበብ የሆነ። *ዜና አንባቢ።*

አናበበ ግ 1. ዋናውን ፅሁፍ ከቅጂው ጋር አስተያየ፥ አመሳከረ። 2. ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ የተለያዩ ቃላትን በመገጣጠም እንደ አንድ ቃል አድርጎ በድምፅ ጠራ (ለምሳሌ ቤት፥ መንግስት ቤተመንግስት)።

አናባቢ ስ ከአፍ ውስጥ የሚወጣው አየር ሳይቆም ወይም ሳይታገድና ሳይጋጭ በሚወጣበት ጊዜ የሚፈጠር እንደ እ፥ኡ፥... ያሉና ተናባቢ ያልሆነ ድምፅ።

አስነበበ ግ 1. (አንድን ፅሁፍ) ሌሎች እንዲያነቡት አደረገ። 2. ንባብ ወይም አነባበብ አስተማረ።

አስነባቢ ስ በመፃህፍት ማንበቢያ ክፍል ለአንባቢዎች አስፈላጊውን እገዛ የሚያደርግ የቤተ መፃህፍት ሰራተኛ።

***ነበነበ**

መነባንብ ስ በአእምሮ የሚመላለሰን ሃሳብ ለአድማጭ ሳይሆን ለገዛ ራስ ብቻ ጮክ ተብሎ የሚደረግ ንግግር(ትያትር)።

አነበነበ ግ 1. ባለማቋረጥ ተናገረ፡ ቀባጠረ። 2. በፍጥነት አነበበ። 3. አጉተመተመ፡ ደገመ።

አነብናቢ ቅ (በድብ) ምላሰኛ፡ ነገረኛ።

ነበዘ^{1} ግ 1. መረዘ፡ አቀለመ፡ አመነቸከ። *ልጅቱ ልብሱን ነበዘው*። 2. ማስተዋል ወይም ማሰብን ተሳነው፥ ፈዘዘ፡ ነፈዘ። 3. ጠቆረ፡ ተበላሸ፡ ማዲያት ያዘው። *ፊቱ ነበዘ*።

ነባዛ ቅ 1. ቀለሙ የተበላሸ፡ የመነቸከ፡ የቸከ (ልብስ)። 2. (በድብ) ነፈዝ፡ ፈዛዛ። 3. ፊቱ የጠቋቆረ፥ ማዲያታም።

ነበዘ^{2} ግ ቀማ፡ መነተፈ።

ተነበዘ ግ ተቀማ፡ ተመነተፈ።

ነቢይ (ብ.ቁ. **ነቢያት**) ስ ወደፊት ሊሆን፡ሊመጣ ወይም ሊደርስ የሚችለውን ነገር አስቀድሞ የሚናገር የእግዚአብሔር ሰው።

ነባሪ "**ነበረ**" ስር ተመ.

ነባራዊ ዝ.ከ.

ነባር ዝ.ከ.

ነባዛ "**ነበዘ**^{1}" ስር ተመ.

ነቤሳ ስ በበረሃ አካባቢ የሚገኝ አነስተኛ የእፅዋት አይነት።

ነብረድ "**ንቡረእድ**" ን ተመ.

ነብራራ "**ነበረረ**" ስር "**ነበረር**" ን ተመ.

ነብር ስ 1. መልኩ ቢጫማ መደብ ይዞ እንደ ቀለበት ክብ የሆኑ ጥቋቁር ነጠብጣቦች ያሉበት፡ ረዥም ሽንጥና አጫጭር እግሮች ያሉት፡ በሲኻ በቋጥኝና በዋሻ ውስጥ የሚኖር ሃይለኛና ቁጡ የሆነ ስጋ በል አውሬ (ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)። 2. (ዘይ.) በጣም ቁጡ። *ባሏ ነብር ነው ትፈራዋለች*።

ነብርማ ቅ ዝንጉርጉር፡ መልኩ ነብር የሚመስል።

ነብሮ ስ የነጭና የቀይ ድብልቅ የሆነና ከበሬ ጡንቻ ላይ የሚገኝ የስጋ አይነት።

ነቦጨ ግ ወድቆ ተሰበረ።

ነተረ^{1} ግ 1. ብዙ በመቆየቱ በሰሰ፥ ኮሰተረ (ጠላ፣ ጠጅ)። 2. ሆረጠ።

ነተረ^{2} ግ ወጠረ፡ ነፋ፥ ቀበተተ (ሆድን)።

ነተረከ ግ ነዘነዘ፡ ጨቀጨቀ።

ነትራካ ቅ (በድብ) ነዝናዛ፡ ጨቅጫቃ።

ንትርክ ስ ንዝንዝ፡ ጭቅጭቅ።

ተነታረከ ግ ተነዛነዘ፡ ተጨቃጨቀ።

አነታረከ ግ አነዛነዘ፡ አጨቃጨቀ።

ነተበ ግ ሳሳ፡ ተጎዳ፥ ማለቅ ጀመረ (ልብስ)።

ነት ስ ለምንጣፍ ወይም ለመተኛ የሚሆን የለፋ ወይም የለሰለሰ የከብት ቆዳ።

ነት ይንካው (ነገሩ) ይዋል ይደር፡ ይመከርበት፡ ይታሰብበት።

–ነት ቅፅል ወይም ስም በሆነ ቃል መድረሻ ላይ እየተቀጠለ ረቂቅ ስምን ለመመስረት የሚያገለግል ምእላድ፤ ለምሳሌ ኢትዮጵያዊነት፥ እናትነት፡ ደግነት፡...።

ነትራካ "**ነተረከ**" ስር ተመ.

ነነዌ (**ነይነይ**) ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ከሁዳዴ ፆም መባቻ አስራ አራት ቀን ያህል ቀደም እየተባለ የሚፆም የሶስት ቀን የፆም ጊዜ።

ነን (አፍ. "**አይደለንም**") "**ነው**" ን ተመ.

ነኝ (አፍ. "**አይደለሁም**") "**ነው**" ን ተመ.

ነኝ ባይ ቅ እንዲህ ነኝ፡ እንዲህ ነበርኩ እያለ ራሱን የሚያኩራራ፣ ጉረኛ።

ነከረ ግ 1. ዘፈቀ፡ ከተተ። 2. ዘፈዘፈ፡ አራሰ። 3. አጠመቀ። 4. አጠቀሰ።

ነክረው ያወጡት (ዘይ.) ሞኛሞኝ፡ ቂላቂል።

ነክርት(ንክርት) ዝ.ከ.

ንክር ቅ 1. በውሃ እንዲረጥብ ወይም እንዲርስ የተደረገ። 2. (ዘይ.) ቂል፡ ሞኝ።

ተነከረ ግ 1. ተዘፈዘፈ፡ ውሃ ውስጥ ሆነ። 2. (ዘይ.) ተዘፈቀ፡ ተከተተ። *እዳ ውስጥ ተነከረ*። 3. ተጠመቀ።

ነከሰ ግ 1. በጥርሱ ያዘ፥ ወጋ፥ አጣበቀ። 2. በጥርሱ ቦጨቀ፡ ቦተረፈ። 3. ነደፈ፡ወጋ፥ ጠቅ አደረገ (እባብ)። 4. አጣብቆ ያዘ፡ አላንቀሳቅስ አለ (ሞተር)።

ነክሶ ያዘ 1. ጠመደ፡ ጠላ፡ ክፉኛ መርዝ ያዘ። 2. አልለቅም አለ፡ አጥብቆና አጠንክሮ ያዘ።

ንክሻ ስ በጥርስ መቦጨቅ፡ መውጋት፡ መዘንጠል።

ተነከሰ ግ ተቦጨቀ፡ ተቦተረፈ፡ ተበላ። *ልጁ በውሻ ተነከሰ*።

ተናከሰ ግ 1. በጥርሱ ነከሰ፡ ቦጨቀ፡ ቦተረፈ። 2. ተጣላ፡ ተጠማመደ።

ተናካሽ ቅ የሚባላ፡ የሚነክስ (ለምሳሌ. ውሻ)።

አናከሰ ግ 1. እርስ በእርስ አንዱ ሌላውን አጥብቆ እንዲይዝና በመደጋገፍ ጥንካሬ እንዲያገኝ አደረገ። *[illegible](ግንቡ) ጠንካራ እንዲሆን ድንጋዮቹን እያናከሱ መካብ ያስፈልጋል*። 2. (ዘይ.) አጣላ፥ አናቆረ።

ነከተ ግ ተሰበረ፡ ደቀቀ።

መንከት ስ ከቁም ነገር የማይገባ፡ ደቃቃ፡ ውዳቂ ነገር።

ነካታ ቅ ደቃቃ፡ ሰባራ።

ንካች ዝ.ክ.

አነከተ ግ 1. ሰበረ፡ አደቀቀ። 2. ደህና አድርጎ ተመገበ።

እንክት አለ ግ ነከተ፡ እንቅሽ አለ።

እንክት አድርጎ በላ ምንም ሳያስቀር ጠርጎ፡ ጨርሶ በላ።

እንክትክት አለ ስብርብር፡ ድቅቅ አለ።

እንክትክት አደረገ ስብርብር፡ ድቅቅ አደረገ።

ነከነከ ግ 1. እንደልቡ በብዛት ተመገበ። 2. በብዛት ለረዥም ሰአት ዘነመ፡ ጣለ። *ዝናሙ ሲነከንከው አደረ።*

ነከነከ (ኖከኖከ)

ነክናካ (ኖክናካ) ቅ 1. ሰባራ በመሆኑ ድምፁ ጥራት የሌለው (ቃጭል፡ ደወል፥...)። 2. ሲናገር የሚነፋነፍ፡ አፍንጫው ችግር ያለበት በመሆኑ ትክክለኛ ድምፅ ለማውጣት የማይችል።

ነካ ግ 1. ዳሰሰ። 2. ጎነጠ፥ ጎሸመ። 3. ጎዳ፡ አሳመመ። *ቅባት የበዛበት ምግብ በልቼ ሆዴን ነካኝ።* 4. ገጠበ፡ አቆሰለ። *ጭነቱ የአህያውን ጀርባ ነካው።* 5. በደለ፡ ተተናኮለ። *የማንን ወንድም ማን ይነካዋል፤* 6. አሽሟጠጠ፡ ሸረደደ፡ ሰደበ። *በነገር ነካ።* 7. ተዳፈረ፡ ነቀፈ። *የሰው ክብር ላትንካ።* 8 በግብረሥጋ አወቀ፡ ተገናኘ። *ያቺን ሴትዮ ከነካ ጀምሮ ልቡ በፍቅር ተይዟል።* 9. አንድን ነገር በብዛት አደረገ፡ አከናወነ። *እስክሲታውን ነካው።* 10. በከለ፡ አበላሸ። *ልብሱን ጭቃ ነካው።*

ያልነካ ይንካሽ አደረጉት ሁሉም ደበደቡት፥ መቱት።

-ነክ ቀመስ፡ -መሰል፥ -ጠቀስ። *ሱፍ ነክ ልብስ እወዳለሁ።*

ነክሀን በገበጣና በቅልቢሽ ጨዋታ ጊዜ አንድ ተጫዋች መጀመሪያ ከነካው ወይም ከነሳው ጠጠር ሌላ በሌላ ጠጠር እንዳይነካ (እንዳይጫወት) በተቃራኒው ወይም በተጋጣሚው አንደበት የሚባል የመከልከያ ቃል።

ንክ ቅ 1. እንከን ያለበት፡ ሰባራ (እቃ)። 2. በከባድ ጭነት ምክንያት ጀርባው የተገጠበ፡ የቆሰለ (አህያ፡ በቅሎ፡ ፈረስ)። 3. የአእምሮ በሽታ ያለበት፡ ቀውስ፡ ወፈፌ።

ንክች አላደርገውም ፈፅሞ አልነካውም፥ አልሞክረውም።

ንክች አድርገኝ መምታት ቀርቶ በጣትህ ዳስስ ወይም ነካ ብታደርገኝ ጉድህ ይፈላል ለማለት በጠብ ጊዜ ለጠበኛ የሚሰጥ የማስጠንቀቂያ ቃል።

ንክኪ(ንክክ፥ ንክኪት) ስ 1. አካላዊ ግንኙነት ወይም መነካካት (የአንዱ ነገር ከሌላው ጋር)። 2. ጥል፡ ፀብ። *ንክኪ ናቸው።* 3. ወዳጅነት፡ ትውውቅ (የግብረሥጋ)። 4. (ኦ.ኦ.ተ.ቤ.) በፆም ቀን ከስጋ ወይም ከቅቤ ጋር ተነካክቶ የተገኘ እቃ ወይም ምግብ።

ነካካ ግ 1. ደባበሰ፡ ዳሰስ ዳሰስ አደረገ። 2 ተነኮሰ። *በነገር ይነካካኛል።*

የነካካው (የነካው) 1. በመጠኑ አልፎ አልፎ ውሃ ያለበት፡ ውሃ ያረሰው (እንጀራ)። 2. ወፈፍ የሚያደርገው (ሰው)።

ተነካ ግ 1. ወፈፈ፡ ቀወሰ፡ ተለከፈ። *ጤነኛ አይደለም ተነክቷል።* 2. ተጎዳ። *ስሜቱ በሃዘን ተነካ።*

ተነካካ ግ 1. እጅ አረፈበት፡ በእጅ ተዳሰሰ። 2. ተበከለ። *የፆሙ እቃ በስጋ ተነካካ፤* 3. ተዋወቀ (በግብረሥጋ)። 4 ተቃቃረ፡ ተቀያየመ፡ ተጣላ። 5. ተፋሰሰ፡ በካከኑ፡ ተላላሰ። *ዱቄት ተነካካ፤* 6. ተጎነተለ። *እሳትና ድሃ ሲነካኩት አይወድም።*

አነካካ ግ 1. አንዱን አካል ከሌላው ጋር አገጣጠመ፡ አገናኘ። 2. አቀያየመ፡ አጣላ፡ አጋጨ። 3. የፍስኩ ምግብ (ስጋና ቅቤ) ለፆም ከሚሆነው ምግብ ወይም እቃ ጋር እንዲገናኝ አደረገ፡ በከከለ። 4. አብቃቃ፡ በመጠኑ ተጠቀመ። *ብዙ ወጥ ስለሌለ እያነካካ በላ።*

አነካኪ ቅ ነገረኛ፥ ከሰው ጋር የሚያቀያይም፡ የሚያጣላ።

አናካ ግ አነካካ።

አስነካ ግ 1. በመድሃኒት አሳመመ፡ ጉዳት ላይ ጣለ። *ሰውየውን መድሃኒት አስነካው።* 2. አንድን ድርጊት በደንብ አከናወነ፡ ሰራ። *ዘፈኑን አስነካው።*

ነኪታ "**ነከተ**" ስር ተመ.

ነኪ "**ነካ**" ስር ተመ.

ነክናካ "*ነከነከ**" ስር ተመ.

ነኮረ ግ ተቆራረሰ፡ ተፈረፈረ፥ እንኩሮ ሆነ።

አነኮረ ግ 1. ለጠላ ጠመቃ ዝግጅት እንዲሆን ተቆልቶም ሆነ ሳይቆላ የተፈጨን የገብስ ወይም የበቆሎ፡... ዱቄት እንደ በሶ ከውሃ ጋር ካሸ በኋላ በሰፊ ምጣድ ላይ አድርጎ እስኪበስል ድረስ እያገላበጠ አመሰ። 2. ከምጣዱ ላይ ሳይቆራረስ በደህና መውጣት የሚኖርበት እንጀራ ወይም ዳቦ ከጥንቃቄ ወይም ከሙያ ማነስ የተነሳ እየተቆራረሰ እንዲወጣ አደረገ። 3. መነሳት የሌለበትን ሃሳብ በማንሳት ነገር አበላሸ።

እንኳራ ቅ ነገር የሚያበላሽ፥ የሚዘባርቅ።

እንኩሮ ስ 1. በውሃ ተበስብሶ ምጣድ ላይ እየተገላበጠ እንዲበስል የተደረገና ለጠላ የሚሆን ዱቄት። 2. ከምጣድ ላይ በደህና ሁኔታ መውጣት የነበረበት የእንጀራ ወይም የዳቦ ቁርስራሽ፥ ስብርባሪ። 3. (ዘይ.) ቂላቂል፥

አነጋገሩ ጅል፥ ዘባራቂ፡ ነገረ ዘንቃላ።

ነኮተ ግ ደቀቀ፡ መሸከ፡ ተሰባበረ።

ንኳታ ቅ ደቃቃ፡ ስባሪ።

አነኮተ ግ 1. አደቀቀ፥ አመሸከ። 2. እንኩቶ አዘጋጀ።

እንኩቶ ስ 1. እረኞች ከብት በሚጠብቁበት አካባቢ ተሰብስበው በአንድነት የሚበሉት ከነአገዳው ወይም ከነብሩ በእሳት ተለብልቦ የበሰለ የአተር ወይም የባቄላ ወይም የገብስ፡... እህል። ቅ 2. (ዘይ.) የማይረባ፡ ምንም ሊፈይድ የማይችል።

***ነወረ**

ነውር ቅ 1. በህብረተሰቡ ባህልና እምነት መሰረት እንደ መጥፎ ነገር የሚታይ፡ የሚቆጠር (ድርጊት፥ ምግባር፥...)። ስ 2. ገመና። *ነውርህን ሊታሳይ።*

ነውር ነው 1. ፀያፍ ፡ መጥፎ ነው። 2. ተገቢ አይደለም፡ ጥፋት ነው።

ነውር ጌጡ ነውር የሆነ ነገር ሲሰራ የማያፍር፥ ያሉኝ አይል(ሰው)።

ነውረኛ ቅ መጥፎ ፡ አፀያፊ ምግባር ያለው፥ ባለጌ።

አነወረ ግ አጣጣለ፡ አንቋሸሸ፡ ነቀፈ፡ ነውረኛ አደረገ።

አስነወረ ግ 1. ነውረኛ አደረገ። 2. አማገጠ፡ አባለገ፡ ደፈረ (ሴትን በግብረ ስጋ)። 3. የሚያስከፋ፡ የሚያስቀይም ሆነ።

አስነዋሪ ቅ አፀያፊ፥ አሳፋሪ።

ነወር(ኖር) ሰዎች ተቀምጠው ወደ አሉበት ቦታ በመቅረብና ሰላምታ በመስጠት ላይ ያለ ሰው፡ ተቀማጮቹ ብድግ ብለው "ይቀመጡልን" ለማለት ለሰውየው የሚያቀርቡት የአክብሮት መግለጫ ቃል።

ነወር አለ ወደአጠገቡ በመምጣት ላይ ያለን ሰው ከመቀመጫው ተነስቶ በአክብሮት ተቀበለ፤ ይቀመጡ ብሎ ጋበዘ።

***ነወጠ**

ነውጥ ስ 1. ሁከት፡ ብጥብጥ፥ ሽብር። 2. ርደት፡ ንቅናቄ (የመሬት ነውጥ)።

ነውጠኛ ቅ 1. ሁከት ፈጣሪ፥ ረብሸኛ። 2. አሸባሪ።

ተናወጠ ግ 1. ተንቃነቀ፥ ራደ። 2. ታወከ፡ ተበጠበጠ፡ ተሸበረ።

አናወጠ ግ 1. አራደ፡ አንቃነቀ፡ አንቀጠቀጠ። 2. አወከ፡ በጠበጠ፡ አሸበረ።

ነዋሪ "ኗሪ" ን ተመ.

ነው (አፍ. **አይደለም**) ግ 1. ምንነትን ወይም ማንነትን፡ መጠንን፡ አይነትን፥ ግብርን፥ ሁኔታን፡... ለመግለፅ ከሚነገሩ ቃላት ጋር እየተጎዳኘ የሚነገር የአሁን ጊዜ የመሆን ግስ። *ኢትዮጵያዊ ነው/ረዥም ነው/ቀይ ነው/ደግ ነው/ጤናማ ነው።* 2. በተወሰነ ስፍራ ወይም ሁኔታ ላይ መሆንን ወይም መገኘትን ለማመልከት ወይም ለማወቅ ከተለያዩ ቃላት ጋር እየተጎዳኘ የሚነገር ቃል። *አልጋ ላይ ነው/በሥራ ላይ ነው።* (በየመደቡ ሲዘረዘር፥ 1ኛ መደብ ነጠላ ቁጥር "ነኝ"፡ ብዙ ቁጥር "ነን"። 2ኛ መደብ ነጠላ ቁጥር፥ ተባእታይ ፆታ "ነህ"፤ አንስታይ ፆታ "ነሽ"፤ ብዙ ቁጥር "ናችሁ"። የአክብሮት "ነዎት"። 3ኛ መደብ ነጠላ ቁጥር አንስታይ ፆታ "ናት" (ነች)፤ ብዙ ቁጥር ወይም የአክብሮት "ናቸው")።

ነውረኛ "*ነወረ" ስር ተመ.

ነውር ዝ.ከ.

ነውጠኛ "*ነወጠ" ስር ተመ.

ነውጥ ዝ.ከ.

ነዎት (አፍ. **አይደሉም**) "ነው" ን ተመ.

ነዘረ^{1} ግ 1. በጣት ሲነኩት ወይም ሲገርፉት ከፍ ያለ ሙዚቃዊ ድምፅ ሰጠ (የበገና ወይም የክራር ጅማት)። 2. ሰውነትን የንዝረት ስሜት ተሰማ። 3. ጠዘጠዘ፥ እየደጋገመ ወጋ (የቁስል ህመም)።

ንዝረት ስ ከኤሌክትሪክ ሽቦ ጋር በሚደረግ ያልታሰበ መነካካት ወይም እንደ ክርን ያሉ ገላዎች በሚመቱበት ጊዜ የሚሰማ ሰውነትን የሚወር ድንገተኛና ጊዜያዊ የህመም ስሜት።

አነዘረ ግ በመርገብገብ ሙዚቃዊ ድምፅ እንዲፈጠር የበገናን ወይም የክራርን ጅማት በጣቱ ገረፈ፡ መታ።

ነዘረ^{2} ግ ለመምታት በሰው ወይም በእንስሳ ላይ በትር ወይም ሌላ ጎጂ ነገር አሳረፈ፥ ጣለ።

ነዘነዘ ግ 1. ጨቀጨቀ፥ ነተረከ። 2. ደጋግሞ በመጠየቅ፥ በመለመን አሰለቸ፡ አስመረረ። 3. ጠዘጠዘ፥ ነዘረ፡ አመመ(ቁስል)።

ነዝናዛ ቅ ጨቅጫቃ፥ አንዴ ነገር ከጀመረ በቶሎ የማይለቅ ፣ ችክ ።

ንዝንዝ ስ ጭቅጭቅ፡ ንትርክ።

ንዝንዘኛ ቅ ተጨቃጫቂ፡ ተነታራኪ ።

ተነዛነዘ ግ ተጨቃጨቀ፥ ተነታረከ።

ተነዛናዥ ቅ ተጨቃጫቂ፡ ተነታራኪ።

አነዛነዘ ግ አጨቃጨቀ፡ አነታረከ።

አነዛናዥ ቅ አጨቃጫቂ፥ አነታራኪ።

***ነዘዘ**

ንዛዥ ስ ትንታ፡ ከሰውነት ጋር ባለመስማማት ወይም በሌላ ምክንያት ከተበላና ከተጠጣ በኋላ

ጥቂት ባፍንጫ በኩል በመምጣት ችግር የሚያስከትል ምግብ ወይም መጠጥ፡፡

እነዘዘ ግ ተዘቅዝቆ በመተኛት ወይም በሌላ ምክንያት የተበላውና የተጠጣው ባፍንጫ ወጣ፡፡

ነዛ ግ 1. ረጨ፤ ፈነጠቀ፡፡ 2. የተወሰነን የእህል መጠን በሰሃ ምጣድ ላይ በተን አደረገ (ለመቁላት)፡፡ 3. አጠፋ፤ ወረሰ፤ አባከነ (ገንዘብን)፡፡ 4. አዛመተ፤ አሰራጨ፤ አዳረሰ (ለምሳሌ ወሬን)፡፡ 5. ስምን በከንቱ አነሳ፤ አጠፋ፡፡ *ስሜን እየዞረ ነዛው፡፡*

ንዛት ስ ምጣድ ላይ በአንድ ጊዜ ለመቁላት የሚችል የተወሰነ የእህል መጠን (ለምሳሌ አንድ ወይም ሁለት እፍኝ ጥሬ)፡፡

ነዝናዛ "ነዘነዘ" ስር ተመ.

ነይ ግ በሁለተኛ መደብ፤ በነጠላ ቁጥር፤ (በአንስታይ ፆታ ጊዜ የሚያገለግል የ"መጣ" ትእዛዝ አንቀጽ፡፡ *አንቺ ቶሎ ነይ፡፡*

ነይነይ "ነነዌ" ን ተመ.

ነደለ ግ በሳ፤ ሸነቆረ፡፡

መንደልት ስ 1. የጆሮ መበሻ፡፡ 2. ድጅኖ፡፡

መንደልቶ ስ ሰፊ ወይም ትልቅ የጆሮ ሎቲ፡፡

ነዳላ ቅ ብስ፡ ሽንቁር፡ ቀዳዳ፡፡

ተነደለ ግ ተበሳ፡ ተሸነቆረ፡ ተቀደደ፡፡

ተነዳደለ ግ ተበሳሳ፡ ተሸነቋቆረ፡፡

ነደደ^{1} ግ 1. ተያያዘ፤ ተቃጠለ (እሳት)፡፡ 2. ተቃጥሎ አመድ ሆነ፡፡ 3. በጣም ሞቀ፤ በሙቀት ሃይል ተሰቃየ፡፡

ነዲድ ስ በመቃጠል ላይ ያለ ነገር፡፡ (ለምሳሌ እንጨት)፡፡

ነዳጅ ስ ሞተርን ለማንቀሳቀስ የሚያገለግል በጋዝ ወይም በቤንዚን መልክ የሚገኝ የሃይል ምንጭ፡፡

ነድ ስ የእሳት ነበልባል፤ የእሳት ላንቃ፡፡

ንዳድ ስ 1.በጣም ሃይለኛ ሙቀት፡ ቃጠሎ፡ እሳት፡፡ 2.ትኩሳት ያለበት ወባ፡፡

ማንደጃ ስ 1. እሳትን በቶሎ ለማቀጣጠል የሚረዳ እንደሳር፤ ወረቀት ያለ ተቀጣጣይ ነገር፡፡ 2. እሳትን ጎንበስ ብሎ በአፍ እፍ እያሉ በማቀጣጠል ፈንታ ራቅ ብሎ ትንፋሽን በውስጡ ለማሳለፍና በእሳቱ ወላፈን ሳይጎዱ እሳቱን ለማቀጣጠል የሚረዳ፣ ለዚሁ ተብሎ የሚዘጋጅ የሸንበቆ ቁራጭ፡፡ 3. እሳት የሚነድበት ቦታ፡ እቃ ወይም እሳቱ የሚቀጣጠልበት ቦታ፡፡

ምድጃ ስ 1. ምግብ ለማብሰል እሳት የሚነድበት ቦታ ወይም እሳቱ የሚቀጣጠልበት እቃ፡፡ 2. በጋዝ ወይም በኤሌክትሪክ አማካይነት እሳት ለመፍጠር የሚያስችልና ለምግብ ማዘጋጃነት የሚያገለግል እቃ፡፡

ነደደ^{2} ግ 1. ተበሳጨ፤ በገነ፤ በሸቀ፡፡ 2. ተሰቃየ፤ ተጠመደ (በፍቅር)፡፡

ንዴት ስ ብስጭት፡ ብግነት፤ ብሽቀት፡፡

ንዴተኛ ቅ ብስጩ፤ ቁጡ፡፡

ተናደደ ግ ተቆጣ፤ ተበሳጨ፡ በገነ፡ በሸቀ፡፡

ተናዳጅ ቅ ብስጩ፡፡

አናደደ ግ አስቆጣ፤ አበሳጨ፡ አበገነ፤ አበሸቀ፡፡

አናዳጅ ቅ አብሻቂ ፡ አናዳጅ፡፡

ነደፈ^{1} ግ በደጋን ላይ የተወጠረ ጅማትን በቀል አንጓት እየሳበ በማንዘር ለፈትል የሚዘጋጀውን ጥጥ አፍታታ፡ ንድፍ እንዲሆን አደረገ፡፡

ንድፍ ስ ከፍሬው ተለይቶ፡ በደጋን ተነድፎና እንደቁልል ደመና በስሱ ተከምሮ የሚገኝ፤ ለፈትል ወይም ለእንዝርት የተዘጋጀ ጥጥ፡፡

ንድፍ ይመስላል በጣም ነጭ ነው፡፡

ነደፈ^{2} ግ በወረቀት ላይ ቀየሰ፡ ፕላን ሰራ፡ ሳለ፤ በገረ፡፡

ንድፍ ስ ቢጋር፡ ቅያስ፡ ፕላን፡፡

ነደፈ^{3} ግ 1. ነከሰ፡ በመርዝ ወጋ (ለምሳሌ እባብ)፡፡ 2. ወጋ (በቀስት)፡፡ 3. አመመ፡ አሰቃየ (የመጠዝጠዝ፡ የመውጋት፤ የራስ ምታት ስሜት)፡፡ 4(ዘይ.)ወጋ፤ ጠቅ አደረገ (በነገር) ፡፡

ተነደፈ ግ ተለከፈ፤ ተጠመደ፡ ተመረዘ፤ ተያዘ(በመጥፎ ነገር)፡፡

ተናደፈ ግ ወጋ፤ ጠቅ አደረገ፡፡

ተናዳፊ ቅ 1. መርዘኛና ተናካሽ የሆነ፡፡ 2. (ዘይ.) ተሳዳቢ፤ አሽሙረኛ፡ በነገር ሰውን የሚያስቀይም፡፡

ነዲድ "**ነደደ**^{1}" ስር ተመ.

ነዳ ግ 1. ወደ አስፈላጊው ቦታ ወሰደ (ለምሳሌ እንስሳትን)፡፡ 2. አሽከረከረ፤ ሾፈረ (ለምሳሌ መኪናን)፡፡ 3. (ዘይ.) በብዛት አስቀመጠ (ተቅማጥ)፡፡

መናጆ ስ 1. ብቻውን በመሆኑ እየደነበረ በጉዞ ላይ ችግር ለሚፈጥር አዋኪ ከብት፡ እንደአጃቢ ሆኖ አብሮ እንዲሄድ የሚደረግ ገራም ከብት፡፡ 2. ከሌላው ጋር አብሮ ወይም ሌላውን አጅቦ የሚሄድ፤ አነሂያጅ (ሰው)፡፡

መንጃ ፈቃድ ስ በማሽከርከር ሙያ ለሰለጠነ ሰው የሚሰጥ የሙያ ብቃት ማስረጃ፡፡

ነጅ(ነጂ) ስ 1. እረኛ፡ ወዲያና ወዲህ የሚሄዱ ከብቶችን የሚከተል፡ የሚጠብቅ፡፡ 2. ሾፌር፡ አሽከርካሪ፡፡

ተነዳ ግ 1. ተወሰደ፡ እንዲሄድ ተደረገ(ከብት)፡፡ 2. (ዘይ.) በሌላ ሰው ሃሳብ ተመራ፡፡

ነዳላ "**ነደለ**" ስር ተመ.

ነዳይ(ብ.ቁ.**ነዳያን**) ስ ተመፅዋች፣ ድሃ።

ነዳጅ "**ነደደ**" ስር ተመ

ነድ¹ ግ.ክ.

ነድ² (**ነድ ቀለም**) ስ ፍም የሚመስል የቀይ ቀለም ዓይነት።

ነድ³ ስ እሳት የሚመስል ቀይ ዶቃ።

ነዶ ስ ከነብርኩ (ከነአገዳው) እየታጨደና ሁለት ሁለት ወይም ሶስት ሶስት ጭብጥ በአንድነት እየተደረገ የታሰረ እንደገብስ፣ ስንዴ፣... ያለ የእህል ሰብል።

ነጅ(ነጂ) "**ነዳ**" ስር ተመ.

ነገ "**ነጋ**" ስር ተመ.

ነገለ ግ ከስሩ ተነቀለ፣ ተመነገለ።

ነገረ ግ በአእምሮው የያዘውን ወይም ያሰበውን ለሌላው ገለፀ፣ አሰማ፣ አሳወቀ።

ነገረለት 1.መልእክት አደረሰለት። 2. መሰከረለት ፤ በምስክርነት ረዳው (ረቺ አሸናፊ እንዲሆን)።

ነገረበት 1. አወራበት፣ ለሌላ አሰማበት። 2. መሰከረበት፣ ተረቺ ወይም ተሸናፊ አደረገው።

ነገረው 1. አስረዳው። 2. ሰደበው፣ አዋረደው። *ልክ ልኩን ነገረው*።

ነግሬሃለሁ የቁጣ፣ የዛቻ፣ የማስጠንቀቂያ ሃሳብ መግለጫ ቃል። *ነግሬሃለሁ ከፊቴ ሂድ*።

ነገረ ሰሪ ቅ አሳባቂ፣ ሸውከኛ፣ አቀባጢ።

ነገረ ሰይጣን ቅ ክፉ አሳቢ፣ ተንኮለኛ።

ነገረ ስራ ስ ሁኔታ፣ አካሄድ። *ነገረ ስራው አላማረኝም*።

ነገረ በላ ቅ 1. ነገር የሚያመነጭ፣ የሚያብለሰልስ። 2. ነገር ወዳጅ፣ ነገረኛ። 3. መሠሪ፣ አዋቂ።

ነገረ ዘርቅ ስ ቁምነገር የሌለው ሀሳብ፣ ፌዝ፣ ቀልድ።

ነገረፈጅ ስ ጠበቃ፣ ተሟጋች፣ አቡካቶ።

ነገር ስ 1. ድርጊት፣ ስራ፣ ተግባር። *አይ የሰው ነገር!* 2. ሁኔታ፣ አካሄድ፣ *ነገሩ አላማረኝም*። 3 ጉዳይ። *ያ ነገር ከምን ደረሰ?* 4. ምክንያት፣ ጉዳይ። *ያለ አንድ ነገር ድንገት አገር ለቆ አይሄድም ነበር*። 5. ሙግት፣ ክርክር። *ፍርድ ቤት ነገር አለብኝ*። 6. ጠብ፣ ጭቅጭቅ፣ ንትርክ። *ነገር አያጣውም*። 7. ወሬ፣ ዜና። *የሰማሁት ነገር አለ*። 8. በስም ያልተጠቀሰ እቃን ወይም ጉዳይን እየተኩ የሚነገር ቃል። *አንድ ነገር እገዛልሃለሁ*።

በነገር ጎሸመ ሊሰማው ሰው ሊያስቀይም ወይም ሊያስቆጣ የሚችል ነገር በቀጥታ ሳይሆን በተዘዋዋሪ ወይም በአግቦ ተናገረ።

በነገር ጠለፈ/አጠመደ 1. በንግግሩ፣ በምክሩ፣...ሌላውን አሳሳተ፣ ስህተት ላይ ጣለ። 2. አንዱ የተናገረውን አጣምሞ በመተርጎም ሌላ አቅጣጫ እንዲይዝ አደረገ፣ ወነጀለ።

ነገሩ በሰለ በሚገባ ተብላላ፣ ለፍፃሜ ተቃረበ።

ነገር ለኮሰ ጥል እንዲፈጠር አደረገ፣ ጠብ ቀሰቀሰ።

ነገር ሰራ አሳበቀ፣ አዋሸከ፣ አጣላ።

ነገር ቆሰቆሰ/ጫረ ጠብ ጫረ፣ ነገር አነሳሳ።

ነገር ቋጠረ 1. ዶለተ፣ አሴረ፣ ክፉ ነገር አሰበ። 2. ክፉ ምክር ጠነሰሰ።

ነገር በሆዱ ይዟል ቂም ይዟል፣ ተቀይሟል።

ነገር ተወለደ ያልታሰበ ችግር ተፈጠረ።

ነገር ነገሩን ይዞታል ከሞላ ጎደል ስለ ጉዳዩ ያውቃል፣ ስለ ሁኔታው በመጠኑ ተገንዝቧል፣ ለመሆን ወይም ለመምሰል ሞክሯል።

ነገር አለሙን ትቶታል ለማንኛውም ጉዳይ ግድ የለሽ ሆኗል።

ነገር አመላለሰ አሳበቀ፣ ያንዱን ነገር ለሌላው ነገረ።

ነገር አረገዘ ቂም ያዘ።

ነገር አስከረው በነገር በስጭትና ንዴት ምክንያት ራሱን መቆጣጠር ተሳነው፣ እንደሰከረ ሰው ሆነ።

ነገር አቡኪ ነገር የሚያባብስ ፤ የሚያጣላ፣ ነገር ወዲያና ወዲህ በማመላለስ ሰዎችን የሚያጋጭ።

ነገር አታባዳ (ነውር) ያንዱን ለሌላው እየነገርክ ሰው አታጣላ ፤ አታፋጅ።

ነገር አወጣ ምስጢር አወጣ፣ ተናገረ።

ነገር አወጣ አወረደ አሰላሰለ።

ነገር አዞረ በቀጥታ የተነገረውን ሃሳብ በሌላ ተረጎመ፣ ወደ ላልታሰበበት አቅጣጫ ለወጠ፣ ጠመዘዘ።

ነገር አጥባቂ ቅ ማንኛውም ጉዳይ በጥንቃቄ የሚይዝ፣ በቀላሉ የማይተው።

ነገር ገመደ/ሸረበ/ጎነጎነ/ፈተለ 1. አሴረ፣ ዶለተ። 2. አንድን ነገር ወይም ጉዳይ በቀና መንፈስ በማየት ፈንታ ልዩ ልዩ ትርጉም በመስጠት ቀላል የነበረው ከባድ፣ ቀና የነበረው የተወሳሰበና አስቸጋሪ እንዲሆን አደረገ።

ነገር ጎተተ 1. ያልታሰበ ነገር(ችግር) ውስጥ ገባ፣ ነገር አመጣ። 2. ነገር ቶሎ አልቆርጥ አለ።

ነገር ፈለገ ነገር ጫረ።

ነገርን ነገር ያነሳዋል ስለ አንድ ነገር ሲወራ ወይም ሲወሳ ሌላው ነገር ትዝ ይላል።

ነገር ሸራቢ ቅ አድመኛ፥ ቤረኛ፡ ነገር ጠምዛዥ።

ነገር ቀማሚ ቅ ነገር አዋቂ፡ አሳማሪ፡ ምክር አዋቂ።

ነገር አሽቃች ቅ ጠብ ፈላጊ፡ ጥል ወደ አለበት የሚሳብ።

ነገር ወዳድ ቅ ጠብ ወዳጅ፡ ነገረኛ።

ነገር የበሳ ቅ 1. ነገር አዋቂ፡ አስተዋይ፥ አመዛዛኝ፡ ብዙ የሚያውቅ። 2. ነገረኛ።

[ነገር] ግን መ.ባ. የመጀመሪያውን ሃሳብ ከሚቀጥለው ጋር ለማነጻጸር ወይም በተቃራኒው አንጻር ለመግለጽ የሚያገለግል። *ስራቸው አድካሚ ነው፤ ነገር ግን ክፍያቸው ዝቅተኛ ነው /እሱ ይወዳታል፤ ነገር ግን እሷ ትጠላዋለች/የሚልህን አድምጥ፤ ነገር ግን አትመነው።*

ነገር ጠምዛዥ ቅ በቀና መንፈስ ግልፅና ቀጥተኛ በሆነ መንገድ ለሚቀርበው ሃሳብ ሁሉ ተቃራኒ የሆነ ትርጉም የሚሰጥ፡ ጠማማ፡ ተንኮለኛ።

በነገራችን ላይ በጭውውት ጊዜ ሌላ ጉዳይ በጣልቃ አስገብቶ ለመናገር ሲያስፈልግ እንደ ይቅርታ መጠየቂያ በማድረግ ተናጋሪው ለአድማጭ የሚያሰማው ቃል።

የነገር መንገድ የነገር ስልት፥ የነገር አያያዝ።

የነገር አባት ስ ባልና ሚስት በሚጋቡበት ጊዜ ከእያንዳንዳቸው በኩል የሚቀርብና በውሉ ላይ የሚገኝ፡ አለመግባባት በሚፈጠርበት ጊዜ ለቆመለት ወገን የሚከራከር ሰው።

የነገር ስም ስ (ሰዋ.) ከንግግር ክፍሎች ውስጥ ረቂቅ የሆኑ ስሞች፥ (ለምሳሌ ነፃነት፡ ብርሃን፥...) የሚጠሩበት የስም አይነት።

የነገር ቋት ስ ወሬኛ፥ ነገረኛ።

ነገረተኛ ሙግት፥ ክርክር ያለበት ሰው።

ነገረኛ ቅ 1. ጠብ ጫሪ፥ ተንኮለኛ። 2. ምላሰኛ።

ንግር(ንግርት) ስ አንድ ድርጊት (ከመፈፀሙ በፊት) ወደፊት እንደሚፈፀም በቅድሚያ የተነገረ ሃሳብ፤ ትንቢት።

ንግረኛ(ንግርተኛ) ወደፊት ስለሚሆነው ነገር አስቀድሞ የተነገረለት፥ የተወራለት፥ እንዲህ እንዲህ ይሆናል የተባለለት (ሰው)።

ንግግር ስ 1 አንድ ተናጋሪ ለአድማጩ በቃል የሚያቀርበው ሃሳብ፥ መልእክት፥ አስተያየት፥...። 2. በሰዎች መካከል የሚደረግ። የቃል ጭውውት፥ የሃሳብ ልውውጥ። 3. ጭቅጭቅ፡ ንትርክ። *ያ ጉዳይ በቶሎ የማይፈፀም ከሆነ ከንግግር እንዳያደርሰን እሰጋለሁ።*

ንግግር አያውቅም 1. ሃሳቡን በሚገባ የመግለፅ ችሎታ የለውም። 2. ቃላት ሳይመርጥ አፉ እንዳመጣለት ስለሚናገር ነገር ያበላሻል።

ንግግር አደረገ ስ ሰዎች በተሰበሰቡበት ቦታ ላይ ስለ አንድ ጉዳይ በቃል ወይም በፅሁፍ ሃሳብ፡ መግለጫ፡ ማስረጃ፡... አቀረበ፥ ሰጠ።

የንግግር ቋንቋ ስ 1. ያደባባይ ያልሆነ፥ በንግግር ላይ ብቻ የሚያገለግል ቃል።2. ገና በፅሁፍ ላይ ያልዋለ ቋንቋ።

ተነገረ ግ ተባለ፤ መልእክት፥ ሃሳብ ተላለፈ።

ተነገረው ተረዳ፡ ሰማ። *ያባቱ ሞት ተነገረው።*

የተነገረለት እውቅ፡ የታወቀ።

ትንግርት ስ ጉድ፥ ድንቅ፡ ተአምር።

ትንግርተኛ ቅ ተአምረኛ።

ተነጋገረ ግ 1. ተወያየ፥ ሃሳብ ለሃሳብ ተለዋወጠ። 2. ተጫዋወተ፡ አወራ። 3. ተዋዋለ። *ቤቱን እንዲያድስልኝ ከመሃንዲስ ጋር ተነጋግሬያለሁ።* 4. ተጣላ፡ ተጨቃጨቀ። *ክፉና ደግ ተነጋገሩ።* 5. ታረቀ። *ተኳርፈው የነበሩት ተነጋገሩ።*

ተናገረ ግ 1.ሃሳቡን ገለፀ፡ አሰማ። 2. አወራ፡ ለፈለፈ። 3. አሳበቀ። 4. ተቆጣ፡ አስቀየመ፥ አስከፋ።

ተናጋሪ ቅ 1. ንግግር አዋቂ፥ ጥሩ የንግግር ችሎታ ያለው። ስ 2. ንግግር አድራጊ። 3. (በይ.) ምላሰኛ፥ ለፍላፊ፡ በንግግሩ ሰውን የሚያስቀይም፤ ተሳዳቢ።

አነጋገረ ግ 1. አጫወተ፥ አወራ። 2. ጠየቀ፡ ሃሳብ ተለዋወጠ። *ስለህመሙ ሃኪም አነጋግሬአለሁ።* 3. በቋንቋ የማይግባቡ ሰዎች በአስተርጓሚነት ሃሳብ እንዲለዋወጡ፥ እንዲግባቡ አደረገ። 4 አገናኘ፡ አስማማ፡ አዋዋለ። *ጉዳይህን በቶሎ ሊፈፅምልህ የሚችል ጠበቃ ፈልጌ አነጋግርሃለሁ።* 5. አነታረከ፥ አጨቃጨቀ። *እኔ ካንተ ጋር ምን አነጋገረኝ ያደረግከውን ለሚመለከተው አሳውቃለሁ።*

አነጋጋሪ ቅ 1. አጠያያቂ፥ የሚያወያይ (ነገር፥ ሃሳብ)። ስ 2. አጫዋች፥ ጓደኛ።3. አስተርጓሚ።

አናገረ ግ 1. ጠየቀ፡ አወያየ። 2. አስቀባጠረ፡ አስለፈለፈ።

አናጋሪ ቅ 1. አስቀባጣሪ፥ አስለፍላፊ። 2. ክፉ ተናግሮ የሚያናግር፥ ተንኮለኛ፡ አሳሳች። *ተናግሮ አናጋሪን ያዝልኝ።*

አስነገረ ግ 1. አሳወጀ። 2. ንግርት ጠየቀ። 3. አስጠነቆለ። 4. (ቤ.ክህ.) የተማሪዎችን ቅኔ እየሰማ አረመ፡ አስተካከለ፡ አስተማረ። ፡

ነገሰ ግ 1. ዘውድ በመጫን የሃገር መሪ ሆነ፡ ዙፋን ላይ ተቀመጠ። 2. (ታቦት) በአመት በአሉ

ቀን ወደ ውጪ ወጥቶ ቤተክርስቲያኑን ዞሮ ገባ። 3. አየለ፡ ገነነ።

መንግስት (ብ.ቁ.**መንግሥታት**) ስ 1. የአንድ አገር ህዝብና የግዛት ስርአት። 2. የአንድ አገር ህዝብና ግዛት፡ መስተዳድር።

መንግስት ግልበጣ ስ አንድን መንግስት፡ መስተዳድር በሃይል ከስልጣን ማስወገድ፣ መፈንቀለ መንግስት፣ ኩዴታ።

መንግስተ ሰማይ(መንግስተ ሰማያት) ስ (ሃይ.) ከሞት በኋላ ፃድቃን (ደጋግች) የሚኖሩባት ናት ተብሎ የሚታመንበት ሰማያዊት ቦታ።

ነገስት "ንጉስ" ን ተመ.

ነጋሲ ቅ 1. ነጋሽ፣የነገሰ፡ የሚነግስ። ስ 2. ንጉስ ወይም የንጉስ ልጅ።

ንጉስ (ብ.ቁ. **ነገስት፣ ነገስታት**) ስ 1. በዘውዳዊ አስተዳደር ዙፋን ላይ የተቀመጠ የሃገር መሪ። 2.በአንድ ቡድን ውስጥ ዋነኛ መሪ። *አንበሳ የአራዊት ንጉስ ነው።* 3. እንደ ሰንጠረዥ፣ ዳማ፡ ካርታ ባሉ መጫወቻዎች ውስጥ ከመጫወቻዎቹ ጠጠሮች ወይም ካርታዎች የአንዱ መጠሪያ።

ንግስት (ብ.ቁ. **ንግስታት**) ስ 1 በዘውዳዊ አስተዳደር ዙፋን ላይ የተቀመጠች የሃገር መሪ። 2. የንጉስ ሚስት። 3. በሰንጠረዥ መጫወቻና በካርታ ውስጥ የአንደኛው መጫወቻ መጠሪያ። 4.የንብ አውራ።

ንጉሰነገስት ስ ለእርሱ የሚገብሩ፣ ትእዛዙን የሚቀበሉና በእርሱ ግዛት ስር በንጉስነት ማእረግ ያሉ ንጉሶች የበላይ የሆነ፡ የንጉሶች ንጉስ።

ንጉሳዊ(ብ.ቁ.ንጉሳውያን) ቅ የንጉስ።

ንግስ ስ ታቦት የሚወጣበት ክብረበአል።

መናገሻ ከተማ ስ 1. የአንድ አገር መሪ መኖሪያና የአገሪቱ ዋና ከተማ። 2. የንጉሱ የንግስና ስርአት የሚካሄድበትና ንጉሱ የሚኖርበት ከተማ።

አነገሰ ግ 1. የታቦት በአል በሚከበርበት ቦታ ተገኝቶ የበአሉ ተካፋይ ሆነ። 2. አጋነነ። 3. አኩራራ፡ አተበተ፥ ትእቢተኛ እንዲሆንና አጉል አስተሳሰብ እንዲያድርበት ተገቢ ባልሆነ መስመር መራ፡ አሳደገ፡...።

አንጋሽ ስ 1. የንጉስ የንግስና ስነስርአት በሚፈፀምበት ጊዜ ንጉሱን ቀብቶ የሚያነግስና ስነስርአቱን የሚመራ ካህን ወይም ጳጳስ።2. የታቦት ክብረ በአል በሚደረግበት ቦታ ተገኝቶ የበአሉ ተሳታፊ የሆነ ህዝብ። 3. አጋናኝ። *ወሬ አንጋሽ*።

አንጋገሰ ግ አሞጋገሰ፣ አሞካሸ፡ አዳነቀ።

ነገነገ ግ ከመረ፡ ደረደረ፡ ቆለለ።

*ነገነገ^{1}

አነገነገ ግ ወፈር ባለና አስፈሪ በሆነ ድምፅ ጮሆ፡ የጩሀት፡ የጉምርምርታ ድምፅ አሰማ (የነብር፡ የአንበሳ፡...)።

*ነገነገ^{2}

አነገነገ ግ ተነቃነቀ።

ነገደ ግ 1. የንግድ ስራ ሰራ፣ አካሄደ። 2. በመደብር ውስጥ ሆኖ ወይም ገቢያ ወጥቶ ሸጠ፣ ሸቀጠ።

መነገጃ ስ ለንግድ ስራ የሚያገለግል ማንቀሳቀሻ ገንዘብ።

ነጋዴ ስ በንግድ ስራ የሚተዳደር ሰው።

ንግድ ስ ትርፍ ለማግኘት ሲባል ሸቀጦችን የመግዛትና የመሸጥ፣ አገልግሎት የመስጠት፡ የማምረት ወይም ሸቀጥን በሸቀጥ የመለወጥ ስራ።

ንግድ ምክር ቤት ስ የአንድን አገር የንግድ እንቅስቃሴ ለማበረታታት፡ እንቅፋቶችን ለማስወገድና አመቺ ሁኔታዎች ለመፍጠር፡ በንግድ ስራ ላይ በተሰማሩ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች የሚቋቋም ማህበር።

የንግድ ልውውጥ ስ በአገሮች መካከል የሚካሄድ የተለያዩ ምርቶችን የመግዛትና የመሸጥ ተግባር።

*ነገደ

እንግዳ ስ 1. ያልዋለ፡ ያላደረ ወይም ያልሰነበተ፡ ከሌላ አካባቢ፣ አገር፣ ቤት፣... የመጣ ሰው። ቅ 2. ባይተዋር፡ ባእድ። 3. አዲስ የመጣ ወይም ለአካባቢው አዲስ የሆነ።

እንግዳ መቀበያ ስ 1. የእንግዳ ማረፊያ ወይም መቆያ ክፍል፡ ቤት፣ ቦታ። 2. ለእንግዳ መቀበያ የሚሆን ወይም የሚያገለግል (የክት ልብስ፡ ገንዘብ፣...)።

እንግዳ ተቀባይ ቅ እንግዳ ወዳድ፡ ተንከባካቢ፡ አስተናጋጅ (በመጋበዝ፣ በማጫወት፣...)።

እንግዳ ነገር ስ ቀደም ብሎ ያልተሰማ፡ ያልታሰበ፡ ያልተጠረጠረ ድንገተኛ ነገር።

እንግዳ ደራሽ ስ ሳይታሰብ ድንገት የመጣ እንግዳ።

እንግዳ ኀርብጥ ስ እንደ ምንጣፍ የሚያገለግል ያልተለፋ ደረቅ የከብት ቆዳ።

ተስተናገደ ግ 1. በእንግድነት ተጋበዘ፣ መስተንግዶ ተደረገለት። 2. የሚፈልገው ጉዳይ እንዲፈፀምለት ተደረገ።

መስተንግዶ ስ 1. ተጠርቶ ወይም ሳይጠራ በእንግድነት ለመጣ ሰው የሚደረግ ግብዣ። 2. እንግዳ አቀባበል፡ የእንግዳ አቀባበል ስነስርአት።

አስተናገደ ግ 1. በእንግድነት ተቀብሎ ጋበዘ። 2. አስተናበረ፡ ባለጉዳዩን በመቀበል አስፈላጊውን ስራ አከናወነ።

አስተናጋጅ ቅ 1. እንግዳ የሚቀበል፣

የሚጋብዝ። ስ 2. አስተናባሪ።

ነገድ ስ በባህል፣ በኢኮኖሚና በአካባቢ ደረጃ አንድነት ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ያለው፣ ከጎሳ ይልቅ መጠኑ ሰፊ የሆነ ማኅበረ ሰብ።

ነጉሳ "*ነጎሰ" ስር ተመ.

ነጋ ግ 1. ሌሊቱ አልቆ ብርሃን ተተካ፣ ወገግ አለ፣ ጎህ ቀደደ። 2. አለፈ፣ ወጣ። *ክረምቱ ሲነጋ እንመጣለን።*

ነገ(ነግ) ስ 1. ማግስት፣ ከዛሬ ቀጥሎ ያለው ቀን።

ነገ ዛሬ አለ አንድን ድርጊት በጊዜው አልፈፅም አለ፣ አዘገየ፣ ቀጠሮ አራዘመ።

ነግ በኔ አለ ነገሩ በእኔም ላይ ሊደርስ ይችላል ብሎ አሰበ።

ከነገ ነገ አለ አዘገየ፣ ቀን አልቆርጥ አለ፣ ጊዜ አጠፋ።

በነጋታው (በበነጋው) በማግስቱ፣ በሚቀጥለው፣ በሁለተኛው ቀን።

ከነገ በስቲያ ከነገ ቀጥሎ ያለው ቀን።

ከነገ ወዲያ ዝ.ከ.

ነጋ ጠባ ዘወትር፣ ሁልጊዜ።

ነግህ ስ ጧት፣ ማለዳ።

ንጋት ዝ.ከ.

ነጋጋ ግ ንጋት ተቃረበ፣ ጨለማው እየለቀቀ ሄደ።

አነጋ ግ 1. አንድ ቦታ ሆኖ አሳለፈ(ሌሊቱን፣ ክረምቱን)። 2. እንቅልፍ ሳይወስደው አደረ፣ ሳይተኛ ቀረ።

***ነጋ**

ንግ ቅ ሊወልቅ፣ ሊላቀቅ የደረሰ፣ እንክን ያጋጠመው፣ መዛነፍ የደረሰበት (የአጥንት መጋጠሚያ ወይም የማንኛውም አካል መገጣጠሚያ)።

ተናጋ ግ መጀመሪያ ከነበረው ስፍራ (አፈጣጠሩ) ተፋለሰ፣ ተንቀነቀ፣ ተናወጠ።

አናጋ ግ አናወጠ፣ አነቃነቀ።

ነጋሪት ስ እንደ ዋርካ፣ ዋንዛ...ያሉ የዛፍ ግንድ ቅርጫው ተፈልፍሎ የሚሰራ ጎኑ ሰፊ፣ ቁመቱ አጭር የሆነና በአዋጅ፣ በዘመቻ...ጊዜ ይጎሰም የነበረ የከበሮ አይነት (ስእሉን የሙዚቃ መሳሪያ ስር ተመ.)።

ነጋሪት ጋዜጣ ስ የመንግስት አዋጆች የሚወጡበት ጋዜጣ።

ነጋሲ "ነገሰ" ስር ተመ.

ነጋዴ "ነገደ" ስር ተመ.

ነጋድራስ ስ 1. በመንግስት ደረጃ የነበረ የቀድሞ ጊዜ የነጋዴዎች ተቆጣጣሪ፣ አለቃ። 2. ከንግድ ዘርፍ የሚገኘውን የመንግስት ግብር ይሰበስብ የነበረ ሹም።

ነጋጋ "ነጋ" ስር ተመ.

ነግ "ነጋ" ስር "ነገ"ን ተመ.

ነግህ ዝ.ከ.

***ነጎሰ**

ነጉሳ ቅ ሞኝ፣ ጅል።

ነጎል ስ ንፍጥ።

አነጎሰ ግ (ንፍጥን) አፈረጠ፣ አወጣ፣ ተናፈጠ።

ነጎረ ግ በእሳት ቀልጦና ውሃ ተጨምሮበት ከቆሻሻው እንዲለይ ተደረገ (ቅቤ)።

ንጉር ቅ እንዲቀልጥ ተደርጎና ውሃ ተጨምሮበት ከቆሻሻ የፀዳ (ቅቤ)።

ንጉር ቅቤ ስ ከቆሻሻ የፀዳና የተነጠረ ቅቤ።

አነጎረ ግ ቅቤን በእሳት አቅልጦና ውሃ ጨምሮበት በማሰንበት ቆሻሻው ከውሃው ጋር እንዲወገድ አደረገ።

***ነጎተ**

እንጎቻ ስ መጠኑ አነስተኛ እንዲሆን ተደርጎ የሚጋገር እንጀራ።

ተነጎተ ግ እንጎቻ ተጋገረ።

አነጎተ ግ እንጎቻ ጋገረ።

አስነጎተ ግ እንጎቻ አስጋገረ።

ነጎደ¹ ግ ሄደ፣ ተጓዘ፣ እልም አለ።

ነጎዶ(ነጎድ) ስ 1. አንድ ላይ ግር ብሎ የሚበር የወፍ አይነት፣ መቄ። 2. ከመርንት ቦታ እየሸሸ የሚመለስ ብዛት ያለው ጀሌ ጦር።

አነጎደ ግ አስኬደ፣ በብዛት አከናወነ፣ አጣደፈ (ሰራዊትን)።

ነጎደ² ግ ተመታ።

አነጎደ ግ በሃይል መታ።

ነጎዶ "ነጎደ¹" ስር ተመ.

ነጎድጓድ "*ጎደጓደ" ስር ተመ.

ነጓ ግ 1. ጓ፣ ዷ አለ፣ ጮሀ (ጅራፍ፣ ፍንዳታ ...)። 2. ጓ፣ ዷ የሚል ድምፅ በመፍጠር ተሰበረ።

አነጓ ግ 1. አጮሀ፣ አፈነዳ። 2. ሰበረ፣ ሲሰብር ጓ፣ ዷ የሚል ድምፅ አሰማ።

ነጠለ ግ 1. ለየ፣ ለየብቻ አደረገ። 2. ዘረጋ። *የታጠፈውን ነጥለው።*

ነጠላ ስ 1. ከድርና ማግ የሚሰራ፣ እንደ ጋቢ እጥፍ ያልሆነ ሸማ። 2. እጥፍ፣ ድርብ፣ መንታ ያልሆነ ነገር። ቅ 3. ከሁለት እጥፍ ያልሆነ (ዶሮ)። 4. (ዘይ.) ጥባሊስ፣ ከሁለቱ።

ነጠላ ሰረዝ ስ በዝርዝር የሚፃፉ ነገሮችን ለመለያየት የሚያገለግል የስርአተ ነጥብ አይነት፥ ምልክቱም "፥" ወይም "፣" ነው (ለምሳሌ በሬ፥ ስንዴ፥ ገብስ፥...)።

ነጠላ ቁጥር (ሰዋ.) አንድ ብቻውን የሚገኝ ነገር ወይም አካል ብዙነት ካለው ነገር ወይም አካል ተለይቶ የሚጠራበት የቅርፅ ስም። ለምሳሌ "የበጎች" ነጠላ ቁጥር "በግ" የሚለው የስም ቅርፅ ነው።

ነጠላ አረፍተ ነገር ስ (ሰዋ.) አንድ ባለቤትና አንድ አንቀፅ ብቻ የሚገኝበት አረፍተ ነገር። ለምሳሌ "ልጁ አድጓል" የሚለው ነጠላ አረፍተ ነገር ነው።

ነጠላ ጫማ ስ ሽፍን ያልሆነና ተረከዝ የሌለው፥ ብዙውን ጊዜ ለቤት ውስጥ የሚያገለግል የጫማ አይነት።

ንጣይ ቅ ነጠላ የሆነ፥ ብቻውን ያለ።

ንጥል ዝ.ክ.

ተነጠለ¹ ግ 1. ተለየ፥ ተከፈለ፥ ተለይቶ ለብቻ ሆነ። 2. ተዘረጋ።

ተነጠለ² ግ ተለያየ።

ተናጣላ ቅ ብቸኛ፥ ብቻውን የሆነ።

ተናጣላ ሆነ ግ 1. ብቸኛ ሆነ። 2. ከሰራ ተለየ፥ ራቀ። 3. ሳሳ፥ አልፎ አልፎ ብቻ ሆነ (ቡቃያ፥ ፀጉር፥...)።

በተናጠል ተው.ግ. ለየብቻ።

አነጣጠለ ግ አለያየ።

ነጠረ¹ ግ 1. ጠራ፥ ንፁህ ሆነ፥ የሚፈለገው ነገር ከማይፈለገው ተለይቶ እንዲወጣ ተደረገ፥ በእሳት ቀልጦ ተጣራ (ቅቤ፥ ብረት፥...)። 2. ትክክለኛው ነገር ታወቀ፥ ተረጋገጠ። *ዕውነቱ ነጥሮ ወጣ*።

ነጥሮ ወጣ ችግርን፥ መከራን ተቋቁሞ አለፈ፥ ታግሎ አሸነፈ።

ንጣሬ ቅ የቅቤ አር፥ ዝቃጭ።

ንጥር ቅ የጠራ፥ ከቆሻሻ ወይም ከማይፈልግ ነገር የተለየ (ቅቤ፥ ማር፥...)።

እንጣሪ ቅ ከብር፥ ከወርቅ፥... የተለያዩ ጌጣጌጦችን የሚሰራ ባለሙያ።

እንጥረኛ ዝ.ክ.

ነጠረ² ግ መሬት ነክቶ ወደላይ ዘለለ፥ ናረ፥ ጓነ (ለምሳሌ ኳስ)።

ንጥር ንጥር አለ ግ ናር ናር አለ፥ የቁጣ አረማመድ ተራመደ።

***ነጠረ**

ተነጣጠረ ግ ከዳኛ ፊት ቀርቦ ከባላጋራው ጋር ተከራከረ፥ ተሟገተ።

ተነጣጣሪ ቅ ክርክር፥ ሙግት ያለበት፥ ባለጉዳይ።

አነጣጠረ ግ 1. አሟገተ፥ አከራከረ፥ የከሳሽንና የተከሳሽን ማስረጃዎች አነፃፀረ፥ መረመረ፥ አመዛዘነ። 2. አለመ፥ አዘገበ፥ ኢላማ አስተካከለ።

አነጣጣሪ ቅ አስተካክሎ ኢላማውን መምታት የሚችል፥ ተኳሽ።

ነጠረቀ ግ በሃይል መታ።

***ነጠሰ**

እንጥስታ(ንጥሻ) ስ በጉንፋን ወይም እንደበርበሬ ባሉና የሚሰነፍጥ ሽታ ባላቸው ነገሮች ምክንያት ከውሃ አዘል አየር ጋር ከአፍንጫ ውስጥ በከፍተኛ ሃይል ተገፍቶ የሚወጣ ድምፅ።

እንጥስ አለ ግ አነጠሰ።

አነጠሰ ግ በጉንፋን፥ አፍንጫን በሚሰረስር ወይም በሚሰነፍጥ ሽታ ምክንያት ውሃ አዘል አየር ወይም እስትንፋስ ከአፍንጫው ድንገት በሃይል አስወጣ፥ የእንጥስታ ድምፅ አሰማ።

አስነጠሰ ግ 1. አነጠሰ። 2. ለማነጠስ ምክንያት ሆነ።

ነጠቀ ግ 1. ቀማ፥ ወሰደ። 2. በብርጭቆ አገመ (ትንሽ ውሃና ጥጥ ከብርጭቆ ውስጥ አድርጎና ጥጡን በእሳት ለኩሶ ብርጭቆውን ወዲያውኑ የህመም ስሜት ባለበት አካል ላይ በመድፋትና ቆየት ብሎም ብርጭቆውን መንጭቆ በማንሳት)።

ነጣቂ ቅ ቀማኛ።

ንጥቂያ ስ ቅሚያ፥ ዝርፊያ።

ነጠቅ ነጠቅ አለ ግ ፈጠን ፈጠን አለ (በአካሄድ፥ በአነጋገር)።

ተነጠቀ ግ 1. ወደ ሰማይ ወጣ፥ አረገ። *ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን*። 2. ተሰበ፥ ተመሰጠ።

ተናጠቀ ግ 1. ነጠቀ። 2. ተሻማ።

አናጠቀ ግ አሻማ።

ነጠበ ግ 1. ጠብ አለ፥ ወደቀ። 2. ተሳተ፥ ተገደፈ፥ አመለጠ (ነገር ወይም ቃል ከአንደበት)።

ነጥብ ስ 1. አንድን ቃል ከሌላው ቃል ለመለየት በቃላት መካከል የሚደረግ የቀለም ጠብታ ምልክት (፡) ። 2. ፍሬ ነገር። *ነጥብ ነጥቡን ብቻ ንገረኝ*።

ነጠብጣብ ስ 1. በቅደም ተከተል በተራ የተቀመጠ የቀለም ጠብታ ምልክት (....)። 2. የፈሳሽ ጠብታዎች ወይም አነስተኛ ካፊያ።

ተናጠበ ግ የጀመረውን ሳይጨርስ በመካከል እንዲያቋርጥ ሆነ።

ተንጠባጠበ ግ 1. መንጠብ ጀመረ፥ ዝናቡ

ጠብ ጠብ አለ። 2. በየቦታው ወደቀ፣ ተዝረከረከ።

አነጠበ ግ ነጥብ አደረገ፣ ሰራ፣ ጻፈ።

አናጠበ ግ በጣልቃ ገብቶ አቋረጠ፣ አደናቀፈ (ስራን፣ ነገርን)።

አንጠባጠበ ግ 1. መንጠብ ጀመረ። 2. በየቦታው ጣለ፣ አዝረከረከ።

እንጥብጣቢ ቅ 1. የፈሰሰ ጠብታዎች፣ ጠፈጠፍ። 2. ተዝረክርኮ ወይም ወዳድቆ የቀረ።

***ነጠበ**

ተንጠበጠበ ግ 1. ተንቀጠቀጠ፣ ተንዘፈዘፈ (በብርድ ወይም በህመም)። 2. ተሸቀጠቀጠ፣ ጠብ እርግፍ አለ።

አንጠበጠበ ግ አንቀጠቀጠ፣ አንዘፈዘፈ።

ነጠነጠ

አነጠነጠ ግ 1. ሰውነቱ፣ ዳበረ፣ ወፈረ፣ ተመቸው። 2. ጠገበ፣ አረጠረጠ፣ አዘጠዘጠ።

***ነጠፈ**

ምንጣፍ ስ በላዩ ላይ ለመቀመጥ ወይም ለመተኛት ወይም ቤትን ለማስዋብ የሚዘረጋ ቆርበት ወይም ጀንዲ ወይም ስጋጃ፣...።

ንጣፍ ስ 1. ምንጣፍ። 2. የመንገድን ወይም የግቢን አቧራና ጭቃ ለመሸፈን መሬት ላይ የሚደረግ የጠፍጣፋ ድንጋይ ወይም የሸክላ፣... ልባስ። 3. መንግስት ከግለሰብ ለሚወስደው ቦታ በምትክነት የሚሰጠው ሌላ ቦታ።

ተነጠፈ ግ 1. ተዘረጋ ፣ ተስተካከለ (ምንጣፍ፣ አልጋ፣...)። 2. ተረበረበ፣ ተደረደረ። *መንገዱ በድንጋይ ተነጠፈ*። 3. በቁሙ ወደቀ፣ ተጋደመ፣ ተዘረረ።

አነጠፈ ግ 1. ዘረጋ፣ አስተካከለ (ምንጣፍን ፣አልጋን፣...)። 2. አለበሰ፣ ሸፈነ (በጣውላ ወይም በሸክላ ወይም በድንጋይ፣... ወለልን፣ መሬትን)። 3.ጣለ፣ ዘረረ (በመምታት)።

አንጣፊ ስ 1. በቤተ መንግስት የእልፍኝ አሽከሮች ሃላፊ የነበረ ሹም። 2. በቤተክርስቲያን ውስጥ ስጋጃ ምንጣፎችን የሚያፀዳና የሚያነጥፍ እንዲሁም ወለሉን የሚጠርግና የሚወለውል ሰራተኛ።

ነጠፈ ግ ደረቀ፣ መስጠት አቆመ።

ነጠፈች ግ ወተት መስጠት አቋረጠች፣ ደረቀች (ለምሳሌ ላም)።

ነጣ ግ 1. ነጭ ሆነ። 2. ፀዳ፣ ጠራ፣ ንፁህ ሆነ።

ነጭ (ብ.ቁ.**ነጫጭ**) ቅ 1. ወተት ወይም ጥጥ የመሰለ። ስ 2. ፈረንጅ። 3. ወተት፣ ጥጥ፣... የሚመስል ቀለም።

በነጭ ይዞታል በቶሎ የሚያባራ አይደለም፣ ቀስ እያለ ነው የሚዘንመው (ዝናም)።

ነጭ ሃር ስ ቀለሙ ነጭ የሆነ የሃር ልብስ አይነት።

ነጭ ለባሽ ስ 1. መተዳደሪያ መሬት ከመንግስት ተሰጥቶት፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ወታደራዊ አገልግሎት ይሰጥ የነበረ የገበሬ ወታደር። 2. የሲቪል ልብስ የሚለብስና በምስጢር የስለላ፣ የወንጀል ክትትል ስራ የሚያከናውን፣ ፖሊስ የህዝብ ደህንነት ሰው።

ነጭ መጋፍጥ ስ ነጭ አዝሙድ።

ነጭ ሽብር ስ በኮሚኒስት ስርአተ ማህበር ውስጥ የስርአቱ አራማጆች፣ ተቃዋሚዎቻቸው የሚፈፅሙባቸውን ጥቃት የሚጠሩበት ቃል ወይም ስም።

ነጭ ሽንኩርት ስ ፍሬው ነጭ ሆኖ እንደቀይ ሽንኩርት በመሬት ውስጥ የሚፋፋና የሚያኮርት፣ ሃይለኛ ሽታና ጣእም ያለውና አብዛኛውን ጊዜ ለምግብ ማጣፈጫነት የሚውል የተክል አይነት (ስእሉን ሽንኩርት ስር ተመ.)።

ነጭ አዝሙድ ስ ፍሬው ነጭ የሆነ የቅመም አይነት።

ነጭ(ነጩ) ዝንጀሮ ስ በጥቂቱ ቡናማ ቀለም የሚለበበት ሆኖ እመድማ መልክ ያለው፣ መቀመጫው መላጣ የሆነና በቆላ አካባቢ በቁጥቋጦ ውስጥ የሚኖር፣ በኢትዮጵያና በሱማሊያ ውስጥ ብቻ የሚገኝ የዝንጀሮ አይነት።

ነጭ ደመና ስ የውሃ ነጠብጣብ ይዘቱ በጣም ዝቅተኛ የሆነና ጥጥ መስሎ የሚታይ የደመና አይነት።

ነጭ ጤፍ ስ ፍሬው ነጭ የሆነ የጤፍ አይነት።

ነጫጭባ ቅ (ስድብ) ሰውነቱ ወዘና የሌለው፣ አመዳም (ሰው)።

ነጭሎ ስ በዴጋና በወይና ደጋ የሚበቅል ቅጠሉ ነጭ የሆነ የቁጥቋጦ አይነት።

ንጣት ስ ነጭነት። *ንጣቱ ወተት ይመስላል*።

ነጣቂ "ነጠቀ" ስር ተመ.

ነጥር(ልጥር) ስ የክብደት መለኪያ(ብዙውን ጊዜ እንደ ማር፣ ቅቤ፣ ወርቅ፣... ለመሳሰሉ) አንድ ነጥር አስራ ሁለት ወቄት ያህል ነው።

ነጥብ "ነጠበ" ስር ተመ.

ነጨ ግ 1. ነጠቀ። *ማጭድ ስለሌለው በእጁ ሳር ነጭቶ ይዞ መጣ*። 2. ዘነተረ (ሲጋን በጥርስ)። 3. ጋጠ፣ በላ (ከብት ሣርን)። 4. ፈተገ፣ መሰጠ፣ ሳጠ (ፈትን በሾለ ነገር በመፈግፈግ)። 5. ገረፈ፣ ሸነቆጠ (በአለንጋ፣ በአርጩሜ)። 6. ቀምቶ፣ አታሎ፣ በቁማር አሸንፎ፣... ወሰደ (ገንዘብን)።

ተነጨ ግ ተነቀለ፣ ተጎሰሰ(ፀጉር)። 2- (ገንዘቡ) ተበላ፣ ተወሰደ (በቁማር፣ በቀማኛ፣...) ።

ኣናጨ ግ አበሳጨ፡ አናከሰ፡ አጨቃጨቀ።

ነጨሬ(ነጨር) ቅ አመለ ነጭናጫ፥ ከሰው የማይስማማ።

***ነጨነጨ**

ነጭናጫ (ነጨንጭ) ቅ አመለቢስ፥ ጨቅጫቃ፡ ብስጩ።

ንጭንጭ አለ ግ ተነጫነጨ።

ተነጫነጨ ግ ተበሳጨ።

አነጫነጨ ግ አበሳጨ፡ አመል ነሳ።

ነጫጭባ "ነጣ" ስር ተመ.

ነጩ ዝንጀሮ "ነጣ" ስር "ነጭ ዝንጀሮ"ን ተመ.

ነጭ "ነጣ" ስር ተመ.

ነጭሎ ዝ.ከ.

***ነፀረ**

ንፅፅር ስ አንድን ነገር ወይም ሁኔታ ከሌላው ጋር የማስተያየት፥ የማወዳደር፥ የማመዛዘን ድርጊት።

አንፃር ስ ትይዩ፥ አኳያ፥ ፊትለፊት። *ቤታችን ለንፃር ለአንፃር ነው።*

ከ __ አንፃር ከ __ አኳያ። *ነገሩን ከሚሰጠው ጥቅም አንፃር መመልከት ይበጅ ይሆናል።*

ተነፃፀረ ግ 1. ተስተያየ፡ ተመሳከረ። 2. ተወዳደረ።

አነፃፀረ ግ 1. አስተያየ፡ አመሳከረ። 2. አወዳደረ።

ነፀብራቅ "*ፀበረቀ" ስር ተመ.

ነፃ ቅ 1. ወንጀል፡ ሃጢአት፥... የሌለበት። 2. እዳ፡ ብድር የሌለበት። 3. ግዴታ፥ ሃላፊነት፥...የሌለበት። 4. የሌላ ያልሆነ ወይም በሌላ ወገን ያልተያዘ (ለምሳሌ መሬት)። 5. ከጭቆና፡ ከባርነት፡ ከተገዥነት የተላቀቀ። 6. እንደፈለገው መሆን የሚችል፥ ቁጥጥር የሌለበት። 7. ያለ ክፍያ፥ በብላሽ የሆነ። *ነፃ ላገልግሎት የሚሰጥ።*

ነፃ ወጣ 1. ወንጀል ሳይገኝበት ቀረ፥ ከቅጣት ዳነ። 2. ከእዳ፥ ከተገዥነት፥... ተላቀቀ። 3. ራሱን ቻለ፡ ራሱን በራሱ ለማስተዳደር በቃ፡ እንዳሻው ለመሆን ቻለ።

ነፃ አውጪ ቅ ህዝቡን (ወገኖቹን) ከጭቆና፡ ከቅኝ አገዛዝ ቀንበር ለማላቀቅ ትግል የሚያካሂድ (ሃይል፡ ሰራዊት፥...)።

ነፃ ትምህርት ስ ትምህርቱን ለመከታተል አስፈላጊ የሚሆኑትን ነገሮች ተማሪው ያለክፍያ (በነፃ) የሚያገኝበት የትምህርት (የመማር) እድል፥ ስኮላርሺፕ።

ነፃ ወደብ ስ የሌላ አገር ሸቀጦችን ያለ ቀረጥ አሳርፎ ተመልሶ የሚወጣበት ወደብ።

ነፃነት ስ 1. አርነት፥ የምንም ነገር ጥገኛ አለመሆን። 2. ሌላውን ሳይነኩ የፈለጉትን ነገር የመስራት፡ የመናገር፡ የመፃፍ፥...መብት። 3. በባእድ መንግስት ወይም በሌላ ሰው ቁጥጥር ስር አለመሆን። 4. ራስን በራስ የማስተዳደር፥ የመምራት ስልጣን፡ መብት።

ነፃ ግ ንፁህ ሆነ።

ንፁህ ቅ 1. የፀዳ፡ የጠራ። 2. ወንጀል፡ ሃጢአት የሌለበት። 3. ቅን፥ ተንኮል፡ ምቀኝነት የሌለው። 4. ከሌላ ጋር ያልተደባለቀ፥ ያልተበረዘ። *ንፁህ ወርቅ።*

ንፁህ ደም ፈሰሰ የሰራው በደል ሳይኖር እንደበደለኛ ደሙ እንዲፈስ ተደረገ።

ንፅህና ስ 1. ንፁህ ሆኖ መገኘት። 2. ከሃጢአት፡ ከወንጀል ነፃ መሆን።

ነፃነት "ነፃ" ስር ተመ.

ነፈለለ ግ ነሆለለ፡ ቂለ፥ ጀለ።

ነፈለል(ንፍላላ) ቅ ነሁላላ፡ ቂል፡ ጅል።

ተንፋለለ ግ ተንኋለለ፡ ቂለ፡ ተጃጃለ(ሲናገር)።

አንፋለለ ግ አንኋለለ፥ አቂለ፡ አጃጃለ።

ነፈረ ግ 1. በጣም ሞቀ፡ ፈላ፡ ተፍለቀለቀ፥ እንደ እሳት የሚያቃጥል ሆነ (ውሃ)። 2. በጣም በሰለ፥ ሞከከ (ንፍሮ)። 3. ብዙ ቦታ ላይ ቆሳሰለ፡ ሰውነቱ በቁስል ተወረረ።

ንፍር ውሃ ስ በጣም የሞቀ፥ የፈላ ውሃ።

ንፍሮ ስ ተቀቅሎ በጣም የበሰለ ወይም የሞከከ እንደ ባቄላ፥ አተር፥ ስንዴ ያለ የጥራጥሬ እህል አይነት፤ ምግብ።

ተናፈረ ግ በነገር ተቋሰለ፡ ተባሰለ።

አነፈረ ግ 1. ንፍሮ ቀቀለ። 2. በጣም አቃጠለ። *ሻዩ ምላሴን አነፈረው።*

ነፈረቀ ግ 1. በጣም አለቀሰ፡ ተንሰቀሰቀ። 2. ቁስሉ ፈነዳ፡ መገለ፥ እገር ፈሰሰ።

ነፈረቅ (ንፍራቃ፥ ንፍርቅ) ቅ አልቃሻ።

ተንፋረቀ ግ 1. በጣም አለቀሰ፡ ማልቀሱን አላቆም አለ። 2. በጣም ቆሳሰለ፡ ቁስሉ በእዥና በመግል ተጨማለቀ።

አንፋረቀ ግ 1. አስለቀሰ። 2. በቁስል አጨመላለቀ፥ ቁስል በቁስል አደረገ።

ነፈሰ ግ 1. ነፋስ ተነሳ፡ ተንቀሳቀሰ፥ ሽው ሽው አለ። 2. ተሰራጨ፥ ተዛመተ፡ ተነዛ (ወሬ)። 3. (በይ.) በጊዜያዊ ፍቅር ከነፈ።

ነፈሰበት 1. በተገቢው መንገድ ሳይከደን በመቅረቱ ተበላሸ (ለምሳሌ. ጠላ፥ እንጀራ)። 2. ወቅቱ፡ ጊዜው አለፈበት፡ ተበላሸ። *የነፈሰበት ወሬ።*

ነፋስ(ንፋስ) ስ 1. በሃይል የሚንቀሳቀስ፡

የሚከንፍ አየር። 2. (ዘይ.) ሀ. ፈጣን፥ ሯጭ። ለ. ከውካዋ፥ እረፍተቢስ።

ነፋስ መታው 1. በእሸት ደረጃ ላይ ያለው ሰብል በሚገባ ከመጎምራቱና ከመብሰሉ በፊት ተስማሚነት የሌለው ነፋስ ስለገረፈው ፍሬው ሳሳ፥ ቀጨጨ። 2. አየር እንዲያገኝ፥ እንዲነፍስበት ተደረገ።

ነፋስ ተቀበለ ከመኖሪያ ቤቱ ወይም ከአካባቢው ራቅ ብሎ በመሄድ ተንሸራሸረ፥ ተዝናና።

ነፋስ እንዳይወስደው እንዳያበረው፥ እንዳይዛመት(ወሬ)።

ነፋስ ገባቸው ተቀያየሙ፥ ፍቅራቸው ተቋረጠ፥ ተለያዩ።

ነፋስ ያልነካው ወሬ ብዙ ሰው ያልሰማው አዲስ ወሬ።

ነፋሻ ቅ 1. ተስማሚ የሆነ ነፋስ ያለበት (ቦታ)። 2. ነፋስ የሚበዛበት (ቦታ)።

ንፋሽ ስ ከደህናው እህል ተለይቶ እንዲወጣ የተደረገ ብጣሪ፥ ግርድ፥ አሰር።

ተናፈሰ ግ 1. የታመቀው፥ የታሸገው ነገር (እቃ፥ ልብስ፥...) ተከፍቶ ወይም ተንጠልጥሎ አየር እንዲያገኘው ተደረገ። 2. ነፋስ ተቀበለ፥ ተዝናና፥ ተዘዋወረ፥ ተንሸራሸረ። 3. ተሰራጨ፥ ተነዛ (ወሬው)። 4. ተፀዳዳ፥ አይነምድሩን፥ ሽንቱን ለማስወገድ ወደ መፀዳጃ ቤት ገባ ወይም ገለል ወዳለ ቦታ ሄደ።

መናፈሻ ስ 1. ለነፋስ መቀበያ የተሰራ ሰገነት። 2. ነፋሻ አየር፥ አትክልትና ለምለም ሳር ያለበት፥ በከተማ አካባቢ ለመዝናኛነት የተከለለ ቦታ፥ መስክ።

አነፈሰ ግ እህልን በሰፌድ አበጠረ፥ ከቆሻሻ ለየ።

አናፈሰ ግ 1. አዲስ አየር እንዲያገኘው አደረገ። 2. አዝናና፥ አንሸራሸረ። 3. ነዛ፥ አሰራጨ (ወሬን)።

አናፋሽ (ወሬ አናፋሽ) ቅ ወሬኛ፥ ወሬ የሚያዛምት።

ነፈነፈ ግ 1. በብዛት ተመገበ፥ ጠጣ። *ምግቡንም ሆነ መጠጡን እስኪበቃኝ ነፈነፍኩት።* 2. ነረተ፥ መታ፥ ደበደበ። *በቦክስ ነፈነፈው።*

*ነፈነፈ^{1}

ነፍናፋ ቅ ሲናገር አፍንጫውን የሚይዘው፥ ኮንኳና።

ተነፋነፈ ግ 1. አፍንጫው እንደልብ አየር የማያስተላልፍ በመሆኑ ሲናገር ድምፁ ጥራት የሌለው ሆነ። 2. ብልሽት ስላለው ድምፁ ጥራት የሌለው ሆነ (ለምሳሌ. ሬዲዮ፥ የሙዚቃ መሳሪያ)። 3. አጉተመተመ፥ የቅሬታ፥ የብሶት፥... ንግግር ለገዛ ራሱ ተናገረ፥ አለቃቀሰ።

*ነፈነፈ^{2}

አነፈነፈ ግ አሸተተ፥ አፈነፈነ።

እንፍናፌ ቅ አሳዳጅ፥ ፈልጎ የሚያገኝ (ወሬን፥ ሌባን፥ የተደበቀ ነገርን፥...)።

ነፈዝ ቅ ፈዛዛ፥ ነሁላላ፥ ቂላቂል።

ነፈገ ግ 1. ከለከለ፥ ነሳ። 2. ሰሰተ፥ ተንቀበቀበ።

ንፉግ ቅ (ስድብ) ስስታም፥ ቅቅታም።

ንፍገት ስ ስስት፥ ቅቅት።

ንፍጊያ ዝ.ክ.

ተነፈገ ግ ተከለከለ፥ እንዳያገኝ ተደረገ።

*ነፈጠ

ንፍጥ ስ 1. በጉንፋን ህመም ምክንያት የሚፈጠርና በአፍንጫ ቀዳዳዎች ውስጥ የሚወጣ ዝልግልግ ነጭ ፈሳሽ። 2. (ስድብ) የማይረባ ሰው።

ንፍጣም ቅ 1. ንፍጥ ከአፍንጫው የማይጠፋ (ሰው)። 2. (ዘይ. ስድብ) የማይረባ፥ ጅላጅል (ሰው)።

ተናፈጠ ግ ንፍጡን ከአፍንጫው ጠረገ፥ አፀዳ።

አናፈጠ ግ 1. የሌላውን ንፍጥ ከአፍንጫው ጠረገለት (ለምሳሌ. የህፃንን)። 2. አፍንጫውን መታ። *በቦክስ አናፈጠው* ። 3. ደበደበ።

ነፈፈ ግ ጀለ፥ ጭምጭም ሆነ።

መነፍ ቅ ጅል፥ ጭምጭም።

ነፋፋ(ነፎ) ዝ.ክ.

ነፋ^{1} ግ 1. ቀበተተ፥ ወጠረ (ሆድን)። 2. በአየር ሞላ (ፊኛን፥ ጎማን፥...)። 3. ትንፋሹን በሙዚቃ መሳሪያ ውስጥ በማሳለፍ ሙዚቃዊ ድምፅ እንዲፈጠር አደረገ። *ዋሽንት ነፋ።* 4. በብዛት አጠራ፥ በየቦታው ወሬን አሰራጨ። 5. አንድን ድርጊት ከመጠን ባለፈ ሁኔታ አከናወነ። 6. ቡፍ አለ፥ ተቀበተተ። *እርሾ ስላለበት ዳቦው በጣም ነፋ።*

ንፋው ቅ (ስድብ) ውሽታም፥ ወሬኛ።

ተነፋ ግ 1. አበጠ፥ ተቀበተተ (የተጎዳ ገላ)። 2. (ዘይ.) በቁጣ ወይም በኩርፊያ ተከመረ፥ አሁጠ፥ ተነረተ።

ነፋ^{2} ግ ጥሬውን ከቆሻሻ በወንፊት ለየ፥ አጠራ። *ዱቄት ነፋ።*

ንፌት(ንፌት) ስ እህል ወይም ዱቄት በሚነፋበት ጊዜ በመጨረሻ ከወንፊቱ ላይ የሚቀረው አሰር፥ ቆሻሻ።

ነፋስ "ነፈሰ" ስር ተመ.

ነፋሻ ዝ.ክ.

ነፍላላ "**ነፈለለ**" ስር ተመ.

ነፍረቃ "**ነፈረቀ**" ስር "**ነፈረቅ**" ን ተመ.

ነፍሳት ስ 1. የ"**ነፍስ**" ብዙ ቁጥር። 2. እንደትላትል፣ ብረሮ፣... ያሉ ጥቃቅን ፍጥረታት።

ነፍስ (ብ.ቁ.**ነፍሳት**) ስ ስጋ ለባሽ ለሆነ ፍጡር ሁሉ እንደ አንቀሳቃሽ ሞተር የምትቆጠር፥ ከፅንሰት እስከ እለተ ሞት ስጋን ተዋህዳ የምትቆይና በሞት ጊዜ ከስጋ የምትለይ ረቂቅ ህላዌ ፤ ህይወት። *ነፍስ የተለየው ስጋ በድን ነው፤ ህይወት የለውም።*

ለነፍሱ አይሳሳም ደፋር ነው፤ አይፈራም፤ አደጋ ፈርቶ ወደኋላ አይልም።

ለነፍሱ/ለእግዚአብሔር ያደረ ደግ፤ የፅድቅ ስራ የሚሰራ።

በነፍሱ ደረሰ 1. የታመመው፣...ሳይሞት ደረሰ፤ በህይወት አገኘው። 2. ለእርዳታ ደረሰ (በችግር ወይም በአሳሳቢ ሁኔታ ላይ ሳለ)። 3. እቃው፤ ጉዳዩ፣... ሊያልቅ ትንሽ ሲቀረው ደረሰበት።

በነፍስ ተይዟል በጣም ታሟል።

በነፍስ ደረሰ ለችግር በቶሎ ደረሰ፤ ተገኘ።

ነፍሱ ተመለሰ 1. ራሱን አወቀ፤ ዳነ (በህመም ወይም በሌላ ምክንያት ራሱን ስቶ የነበረ)። 2. በረታ፤ ሃይል አገኘ።

ነፍሱ ወጣ(ወጣች) 1. በጣም ደነገጠ። 2. ነፍሱ ተለየችው፤ ሞተ።

ነፍሱ ጥላው ሄደች በጣም ደነገጠ።

ነፍሱን ሳተ 1. በድን ሆነ፤ ደነዘዘ። 2. ማንነቱን ዘነጋ፤ እንደ እብድ ሆነ።

ነፍሱን ሸጠ በነፍሱ ፈረደ፤ ቆረጠ (የሚያጋጥመውን አደጋ ለመጋፈጥ)።

ነፍሱን አወቀ ህመሙ ተሻለው፤ ሰውነቱን ተቆጣጠረ።

ነፍሱ እስኪወጣ ከመጠን በላይ፥ በሃይል። *ነፍሱ እስኪወጣ ይወዳታል።*

ነፍሱን አጥቶ ከመጠን በላይ፥ በሃይል፤ በጣም፤ በትጋት። *ነፍሱን አጥቶ ነው የሚሰራው።*

ነፍስ ሆነ በጣም ተወደደ።

ነፍስ አሳለፈ ሰው ገደለ።

ነፍስ አወቀ አደገ፤ አእምሮው በሰለ (ህፃን የነበረው)።

ነፍስ አዋለ በአምባጓሮ መካከል ገብቶ እንዳይገዳደሉ ጠበኞቹን ገላገለ፤ ጠቡን አበረደ።

ነፍስ የለውም 1. አይረባም፤ ሙትቻ ነው። 2. ቀዥቃዣ፤ ክፉክዋ ነው። 3. በጣም ይዋከባል፤ ይጣደፋል፤ ይሯሯጣል (በስራ ጉዳይ)።

ነፍስ ዘራ ተሻለው፤ አንሰራራ።

ነፍስና ስጋው ተለያየ 1. በጣም ደነገጠ። 2. ሞተ።

የነፍስ ዋጋ ያድርግለት (ምር.) ላደረገው ወይም ለተደረገው መልካም ስራ ብድሩን በሰማይ ቤት እግዚአብሄር ይክፈለው።

ነፍሰቢስ ቅ 1. ድንጉጥ። 2. ችኩል፤ ቀዥቃዣ። 3. ደፋር።

ነፍሰ ገዳይ ቅ 1. የሰው ነፍስ ያጠፋ፤ ሰው የገደለ። 2. ጨካኝ፤ አረመኔ።

ነፍሰጡር ቅ እርጉዝ፤ ሽል በሆዷ የያዘች (ሴት)።

[የ]ነፍስ አባት ስ (አ.አ.ተ.ቤ.) የንስሃ አባት፤ በሃይማኖት፤ በመምከር፥... ያንድን ክርስቲያን መንፈሳዊ ህይወት የሚጠብቅ ቄስ ወይም መነኩሴ።

ነፍስ ያለው ቅ 1. አዋቂ፤ ልጅ ያልሆነ፤ ትልቅ(ሰው)። 2. ጥሩ፤ ጠቃሚ። *ለሱቁ ገና ነፍስ ያለው እቃ ገዛ።*

ነፍስ ጥኑ ቅ 1. ቢቀጠቅጡት፤ ቢወጉት ቶሎ የማይደክም ወይም የማይሞት። 2. ጠንካራ፤ መከራ ቻይ።

የነፍስ ልጅ ስ የንስሃ ልጅ።

የነፍስ ወከፍ እያንዳንዱ ሰው በየግል ያለው፤ የሚይዘው፤ የሚያገኘው። *የነፍስ ወከፍ ገቢ/የነፍስ ወከፍ መሳሪያ።*

ነፍናፋ "**ነፈነፈ**" ስር ተመ.

ነፍጥ ስ ጠመንጃ።

ነፍጠኛ ስ ባለነፍጥ፤ የቀድሞ ጊዜ ወታደር።

ነፎ "**ነፈፈ**" ስር ተመ.

ኑ^{1} የ"**ነ**" ፊደል ካእብ ዘር።

ኑ^{2} ግ በሁለተኛ መደብ፥ በብዙ ቁጥር ጊዜ የሚያገለግል የ "መጣ" ትእዛዝ አንቀፅ (እናንተ "ኑ" እንጂ "ምጡ" ወዘተ የሚል አነጋገር በቋንቋው ውስጥ ያልተለመደ ነው)።

ኖሮ "**ኖረ**" ስር ተመ.

ኖስ "**ንኡስ**" ን ተመ.

ኑዛዜ "**ናዘዘ**" ስር ተመ.

ኑግ ስ ፍሬው ጥቁር ሆኖ መጠኑ ተልባ የሚያህል፤ አገዳው መጫ የሚመስል የቅባት እህል አይነት።

ኑፋቄ ስ (ሃይ.) ጥርጣሬ፤ ክህደት፤ መናፍቅነት።

ኒ የ"**ነ**" ፊደል ሳልስ ዘር።

ኒሻን(ሊሻን) ስ ከብር ወይም ከወርቅ፣... የሚሰራና በደረት ላይ የሚደረግ፤ ለሃገር፥ ለወገን፣... አኩሪ ስራ ለሰራ ሰው በሽልማት መልክ የሚሰጥ የክብር ወይም የታላቅ ስራ

ምልክት።

ኒካ ስ የእስልምና ሃይማኖት የጋብቻ ውል ስርአት።

ኒካ አሰረ ተፈጸመ፡ የጋብቻ ውል ተዋዋለ።

ኒኬል ስ መልኩ ግራጫ የሆነ ጠንካራ የማእድን አይነት።

ኒያላ ስ መልኩ በጠቅላላ ግራጫ ሆኖ ትንሽ ቀላ የሚል፡ ከአይኖቹ በታች፡ በአንገቱና በደረቱ ላይ ነጫጭ ሽንትሮች ያሉበት፡ አጋዘን የሚመስልና ቀንዶቹ ጠመዝማዛ የሆኑ ፡ በኢትዮጵያብቻ የሚገኝ የዱር እንስሳ (ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።

ና^{1} የ"ነ"ፊደል ራብእ ዘር።

ና^{2} ግ መደቡ ሁለተኛ፡ ቀጥሩ ነጠላ፡ ጾታው ተበእታይ የሆነን የግስ ባለቤት የሚመለከት የ "መጣ" ትእዛዝ አንቀፅ ("ና" እንጂ "ምጣ" አይባልም)።

ና^{1} **(እና)** መፃ. ቃልን ከቃል ጋር ለማቆራኘት ወይም ለማጣመር የሚያገለግል መስተፃምራዊ ቃል። *ምግብና መጠጥ።*

ና^{2} ስምን ለመመስረት የሚያገለግል ምእላድ (ለምሳሌ ጥብቅ ጥብቅና ፡ ድርቅ ድርቅና፡ ቅልጥፍ ቅልጥፍና)።

ናላ ስ አንጎል፡ አእምሮ።

ናላው ዞረ 1. አእምሮው ተቃወሰ። 2. ተበሳጨ፡ ተናደደ።

ናሙና ስ ብዛት ካለው ነገር ውስጥ ለአይነት ያህል ተመርጦ የሚቀርበው ክፍል። *ከተገኙት ማእድናት ውስጥ ለናሙና ያህል አንዳንድ ይዘን መጣን።*

ናረ ግ 1. ጋነ፡ ነጠረ። 2. ተወደደ፡ ዋጋ ጨመረ።

ንረት ስ ውድነት። *የዋጋ ንረት ያመጣው ቀውስ።*

ናር ናር አለ ቆጣ ቆጣ አለ፡ ሃይለ ቃል ተናገረ።

ናረት "ነረተ^{2}" ስር ተመ.

ናርጅ (ናርድ) ስ ከሆዱ ዘርጠጥ፡ ከላይና ከታች ጠበብ እንዲል ተደርጎ ከግንድ ቁራጭ ተጠርቦና ተፈልፍሎ የሚሰራ የቅቤ ማስቀመጫ።

ናሰ ግ ገነባ፡ ግንብ ሰራ።

ናስ ስ ግንብ።

ናስ ቤት ስ ግንብ ቤት።

ናሴ "ነሃሴ" ን ተመ.

ናስ^{1} "ነሃስ"ን ተመ.

ናስ^{2} "ናሰ" ስር ተመ.

ናስትሮ ስ ያልተሸፈኑ የኤሌክትሪክ ሽቦዎች አደጋ እንዳያደርሱ በመሸፈኛነት የሚያገለግል የፕላስተር አይነት።

ናቀ ግ 1. በዝቅተኛ ደረጃ ተመለከተ፡ እንደተራ ነገር ቆጠረ። 2. ጠላ፡ ተገቢውን ክብር፡ ዋጋ፡ ሳይሰጥ ቀረ።

ናቂ ቅ 1. አንኳሳሽ። 2. ኩሩ።

ንቀት ስ አንድን ነገር አቃሎና ዝቅ አድርጎ የማየት ሁኔታ፤ ለአንድ ነገር ተገቢውን ክብር፡ ቦታ፥ ደረጃ፥...አለመስጠት።

ተናቀ ግ 1. ተንኳሰሰ፥ በዝቅተኛ ደረጃ ታየ። 2. ተጠላ፡ ተገቢውን ቦታ፡ አስተያየት አጣ።

አናናቀ ግ አንኳሰሰ፡ አንቋሸሸ፡ አጥላላ።

አስናቀ ግ ከሌሎቹ ተሽሎ፥ ልቆ፥... በመገኘቱ ሌሎቹ እንዲናቁ አደረገ።

ናበዘ ግ ፈዘዘ፥ ንቃት ወይም ቅልጥፍና አጣ።

ናባዛ ቅ ፈዛዛ፡ ንቃት ወይም ቅልጥፍና የሌለው።

ናት (አፍ. "**አይደለችም**")"**ነው**"ን ተመ.

ናትራ(ናትራን) ስ ነጭ የሽቱ ተክል፥ አሬቲ።

ናቸው (አፍ. "**አይደሉም**")"**ነው**"ን ተመ.

ናችሁ (አፍ. "**አይደላችሁም**")ዝ.ከ.

ናና (ናእናእ) ስ በቅመም መልክ ከሻይ ውስጥ የሚጨመር፡ ጣፋጭ መአዛና ጣእም ያለው አነስተኛ የተክል አይነት።

ናኘ ግ 1. በብዛትና በስፋት ሰጠ፥ አደለ፥ ነዛ። 2. አዘዘ፡ እንደፈለገው አደረገ። *ባለቤት እንግዳ ናኘበት።*

ተናኘ ግ ተሰራጨ፥ ተነዛ፡ ተዘራ። *በሽታው ተናኘ።*

ናወዘ(ናወተ) ግ ተንከራተተ፥ ዋተተ፥ ተንገላታ።

አናወዘ(አናወተ) ግ 1. አንከራተተ፥ አዋተተ፡ አባከነ። 2. አንገለጀጀ፡ አንገላታ (እንቅልፍ)።

ናዘረ ግ ሸፈደ፡ ዛዘነ፡ በወሲብ ፍላጎት ተቅበጠበጠ።

ናዘዘ ግ 1. (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ስልጣነ ክህነት ያለው ካህን በማንኛውም አይነት የስርአተ ፀሎት መጨረሻ ላይ የማሳረጊያ ፀሎት አድርሶና እግዚአ መሃረነ ክርስቶስ እንበል ብሎ ከጨረሰ በኋላ እግዚአብሄር ይፍታህ በማለት ምእመናኑን አሰናበተ። 2. አረጋጋ፡ አፅናና።

ኑዛዜ (ንዝ) ስ አንድ ሰው ከመሞቱ በፊት ሃብቱን ለወራሾቹ ያከፋፈለበት ሰነድ ወይም በሽምግልና ፊት የተናገረው ውርሱን የሚመለከት ቃል።

ኑዛዜው ፈሰሰ የኑዛዜው ቃል ተነገረ፥ ተሰማ፥ ሰነዱ ተነበበ።

የኑዛዜ ወረቀት/ ሰነድ ስ የኑዛዜ ቃል

የተፃፈበት ወረቀት፣ ሰነድ።

ተናዘዘ ግ 1. ከመሞቱ በፊት ንብረቱን በሚመለከት ኑዛዜ አደረገ። 2. የሰራውን ሃጢአት ለካህን ነገረ፥ ማድረግ የሚገባውን ነገር እንዲያደርግ ከካህኑ ትእዛዝና መመሪያ ተቀበለ፤ በካህኑ ፀሎትና ምክር ተፅናና፣ ተበረታታ። 3. (ዘይ.) ምስጢሩን ዘከዘከ፣ አወጣ።

አናዘዘ ግ 1. የአውራሹን የኑዛዜ ቃል ተቀበለ። 2. (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ካህን ፀሎት አድርጎ፣ እግዚአ መሃረነ ክርስቶስ ካለ በሗላ፣ እግዚአብሄር ይፍታህ በማለት ምእመናኑን አፅናና፥ አስናበተ። 3. (ዘይ.) ምስጢር እንዲያወጣ አደረገ።

ናዜራ ስ ሸረሪት የምትመስል፣ መርዛማና ተናዳፊ የሆነች አነስተኛ የነፍሳት አይነት።

ናዝራዊ ስ 1. የናዝሬቱ ወይም የናዝሬት ሰው (ኢየሱስ)። 2. መናኝ፣ ባህታዊ።

ናደ ግ አፈረሰ፣ ገነደረ፣ ጣለ (ግንብን፣ ክምርን፣ ገደልን፣...)።

ናዳ(ናዳት) ስ ከተራራ ላይ ተፈንቅሎና ተንከባሎ ወደታች የሚወርድ ድንጋይ፥ የተራራ ቅራፊ።

ተናደ ግ ፈረሰ፥ ብትንትኑ ወጣ።

ናጠ ግ 1. ቅቤን ከረጋ ወተት ውስጥ ለይቶ ለማውጣት፥ መጀመሪያ ወተቱን እንደ ገንቦ፣ እንስራ፣... ባለ እቃ ውስጥ አድርጎና ከድኖ እቃውን ወዲያና ወዲህ በመግፋት ወይም በመወዝወዝ ወተቱ እንዲንቦጫቦጭና ቅቤው እንዲለይ አደረገ። 2. አወዛወዘ፣ ነቀነቀ፣ አንገላታ።

ተናጠ ግ 1. ተወዘወዘ። 2. ተከራከረ፣ ተጀነነ።

ናጠጠ ግ 1. ፈነጨ፣ ዘለለ፣ ቀበጠ። 2. እጅግ በለፀገ፣ ከበረ። 3. ተንቀባረረ፣ ተኩራራ።

ናጩርት(ናጩርቲያም) ቅ ነጭናጫ፣ ጠባየ መጥፎ።

ናጫ ስ እንደ ሳማ የሚኮሰኩስና የሚያቃጥል ጭገር ያለው፣ ልጡ ለጠንካራ ገመድ መስሪያ የሚሆን የእፅዋት አይነት።

ናፈለ(አናፈለ) ግ በሃይል አመመ፣ አስጨነቀ፣ ትንፋሽ ከለከለ። *ጉንፋን ይዞ ያናፍለኛል።*

ናፈረ(አናፈረ) ግ በቀንዱና በእግሩ መሬት ጫረ፥ ጎደፈረ (ጠብ ወይም ውጊያ የፈለገ በሬ)።

ናፈቀ ግ ተለይቶት የሰነበተውን ወይም የቆየውን ሰው ወይም ሌላ ነገር እንደገና ለማየት፣ ለማግኘት ፈለገ፥ ጓጓ፣ ተመኘ።

ናፋቂ ቅ ሆደ ቡቡ፥ ከዘመድ ተለይቶ መቆየት የማይችል (ሰው)።

ናፍቆት ስ ተለይቶት የቆዩትን ሰው፥ አገር እንደገና የማየት፣ የማግኘት ፍላጎት፣ ጉጉት።

ተናፈቀ ግ በናፍቆት ስሜት ትዝ አለ፣ ታወሰ፣ ተፈለገ።

ተናፋቂ ቅ ከአጠገብ በመራቁ ወይም በቅርብ ባለመገኘቱ በናፍቆት ስሜትና በጉጉት የሚፈለግ፥ ተወዳጅ።

ናፍታ(ናፍጣ) ስ ከባድ መኪናን፣ ሞተርን ለማንቀሳቀስ ወይም ለማገዶነት የሚያገለግል ነዳጅ።

ኔ የ"**ነ**" ፊደል ሃምስ ዘር።

ኔፕቲዩን ስ ከፀሃይ በጣም ርቆ የሚገኝ ስምንተኛው ፕላኔት። በተጨማሪ "**ፕላኔትን**" ተመ.

ን የ"**ነ**" ፊደል ሳድስ ዘር።

-ን 1.በስም መድረሻ ላይ እየተቀጠለ ተሳቢነትን የሚያመለክት ምእላድ (ለምሳሌ ካሳ ልጁን መከረ፣ ስራን ማክበር የሚገባ ነው)። 2.በግስ መድረሻ ላይ እየተቀጠለ የአንደኛ መደብ፣ የብዙ ቁጥር ተሳቢነትን የሚያመለክት ምእላድ (ለምሳሌ በስኣቱ ሄድን፤ለነፃነት ተጋደልን)። 3.በቃል መድረሻ ላይ እየተቀጠለ ተውሳከ ግስን ለመመስረት የሚያገለግል ምእላድ(ለምሳሌ. እለቱን ይገባል)። 4.(ብዙውን ጊዜ በፅሁፍ የሚገኝ) በግስ መድረሻ ላይ እየተቀጠለ ጥያቄን ለማቅረብ የሚያገለግል ምእላድ (ለምሳሌ ስኣቱ ደርሷልን?)።

ንሃስ "**ነሃስ**" ን ተመ.

ንረት "**ናረ**" ስር ተመ.

ንስሃ(ንስሐ) ስ (ሃይ.) 1. ቅጣት፣ መቀጮ። 2. ፀፀት፣ የሰሩትን ሃጢአት አስታውሶ እግዚአብሄርን ይቅርታ የመጠየቂያ፣ ምህረት የመለመኛ መንገድ።

ንስሃ ነው ያስቀጣል፣ ያስኮንናል። *ሰው መግደል ንስሃ ነው።*

ንስሃ አስገባኝ የሰራሁት ሃጢአት ስላለ ቅጣት፣ ኩነኔ አስገባኝ።

ንስሃ ገባ 1. ከክፉ ስራ ወደ መልካም ስራ ተመለሰ፣ በሰራው ሃጢአት ተፀፅቶ የእግዚአብሄርን ምህረትና ይቅርታ ጠየቀ (በመፆም፣ በመስገድ፣...)። 2. መቀጫ፣ ቅጣት ውስጥ ገባ (ሃይማኖት የሚያዘውን መጥፎ ተግባር በመፈፀሙ)።

የንስሃ ልጅ ስ የአንድ የመንፈስ ልጅ፣ መንፈሳዊ ህይወትን በሚመለከት አንድ የተወሰነ ካህን በቋሚነት የሚያስተምረው፥ የሚመክረው፣...ምእመን።

የንስሃ አባት ስ የምእመናን የመንፈስ አባት፣ አበ ነፍስ፣ የነፍስ አባት (ሃይማኖቱ በሚያዘው መሰረት በማስተማር፣ በመምከር የሚጠብቃቸው የተወሰኑ ምእመናን ወይም የመንፈስ ልጆች

ያሉት ካህን)።

ንሳ "*ንሳ" ስር ተመ.

ንስር ስ ትልቅ የአሞራ አይነት (ስእሉን አሞራ ስር ተመ.)።

ንሺ¹ (ንሺቴ) በአንድ ነገር አለመስማማትን ወይም ተቃውሞን ለመግለፅ የሚያገለግል ቃል (የአነጋገር ፈሊጥ)። *አረ ንሺቴ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል።*

ንሺ² (ንሽ) ስ ዘር ለማብቀል ብቁ የሆነና በእርሻ መሬት ውስጥ የሚገኝ የዝናም ርጥበት።

ንሺ ሆነ ዝናም በመጣሉ እርሻው ዘር ለማብቀል የሚያስችል ርጥበት አገኘ።

ንቃት "ናቀ" ስር ተመ.

ንቁ "ነቃ" ስር ተመ.

ንቃሪ "*ነቀረ" ስር "እንቃሪ"ን ተመ.

ንቃሽ¹ "ነቀሰ¹" ስር ተመ.

ንቃሽ² "ነቀሰ³" ስር ተመ.

ንቃተህሊና "ነቃ¹" ስር ተመ.

ንቃቃታም "ነቃ²" ስር ተመ.

ንቃቃት ዝ.ከ.

ንቃት "ነቃ¹" ስር ተመ.

ንቃይ(ንቅል) "ነቀለ" ስር ተመ.

ንቅሳት "ነቀሰ¹" ስር ተመ.

ንቅስ ዝ.ከ.

ንቅናቄ "ነቀነቀ" ስር ተመ.

ንቡረእድ (ንብረድ) ስ በአክሱም ፅዮንና በአዲስ አለም ደብረፅዮን አብያተክርስቲያን ላይ ለሚሾሙ የካህናት አለቆች የሚሰጥ የማእረግ ስም።

ንባብ "ነበበ" ስር ተመ.

ንባብ ቤት ዝ.ከ.

ንብ ስ 1. ተናዳፊ የሆነች፡ አራት ክንፎች ያሏት፡ አበቦችን እየቀሰመች ማር የምትሰራ አነስተኛ የነፍሳት አይነት። 2. (ዘይ.) ትጉህ፡ ታታሪ፡ ባለሙያ።

ንብ [illegible]

ንብስል (ንብአስል) ስ መጠኑ ከጦሰኝ ጋር የሚቀራረብ፡ መልኩ ነጣ ያለና ጥሩ መአዛ ያለው፡ ለቀፎ ማጠኛነት የሚያገለግል የእፅዋት አይነት።

ንብበል ስ የቀይና የአረንጓዴ ዥንጉርጉር መልክ ያለው፡ መንቁሩ ረዢም ብሎ ሹል የሆነና እንደ ንብ፡ ቢራቢሮ፡...ያሉትን እየጠለፈ የሚበላ የወፍ አይነት (ስእሉን ወፍ ስር ተመ.)።

የንብ አውራ (ንግስት) ስ የንብ ስራዊት አለቃ።

የንብ እንጀራ ስ ንቦች በቀፎ ውስጥ የሚያዘጋጁት የእንጀራ ቅርፅ ያለው ሰፋራም የማር ማገር።

የንብ እጭ ስ ገና ክንፍ ያላወጣና በትልነት ደረጃ ላይ ያለ የንብ እንቁላል ፍልፍል።

ንብረት ስ 1. እንደ ቦታ፡ ቤት፡... ያለ የማይንቀሳቀስ ሃብት ወይም ጥሪት። 2. በአጠቃላይ የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ሃብት።

ንብርብር (ንብብር) "*ነበረበረ" ስር ተመ.

ንብዝ "ነበዘ" ስር ተመ.

ንትርክ "ነተረከ" ስር ተመ.

ንኡስ (ኑስ) ቅ አነስ ያለ፡ አነስተኛ የሆነ።

ንኡስ ሃረግ ስ ባለቤትና ማሰሪያ አንቀፅ የሌለው ጥምር ቃል (ለምሳሌ በዛፍ ላይ፡ከምድር በታች፡በክፉ ዘመን፡...)።

ንኡስ አንቀፅ ስ የንኡስ አንቀፅ አይነቶች አምስት ሲሆኑ እነሱም "መፈለግ፡ ፈልጎ፡ ፈላጊ፡ አፈላለግ፡ ፍለጋ" ያሉት የግስ እርባታ ቅርፆች ናቸው። ስማቸውም በቅደም ተከተል፦ አርእስት፡ ቦዝ፡ ግሳዊ ቅፅል፡ ባቢዘርና ጥሬዘር በመባል የሚታወቁት የግስ እርባታ ቅርፆች መጠሪያ።

ንኡስ ከበርቴ ስ በሶሻሊዝም ፍልስፍና አመለካከት መለስተኛ ገበሬዎችን፡ ነጋዴዎችን፡ ባለሙያዎችን፡... የሚያካትት የህብረተሰብ ክፍል።

ንካች "ነከተ" ስር ተመ.

ንክ "ነካ" ስር ተመ.

ንክር "ነከረ" ስር ተመ.

ንክሻ "ነከሰ" ስር ተመ.

ንክች "ነካ" ስር ተመ.

ንክኪ ዝ.ከ.

ንክኪት (ንክክ) ዝ.ከ.

ንዋይ ስ ገንዘብ፡ ሃብት።

ንዋየ ቅድሳት ስ እንደ አልባሳት፡ ፃህል፡ ፅዋ፡...ያሉ በአብያተ ክርስቲያናት ውስጥ

የሚገኙ የተቀደሱ እቃዎች።

ንዛት "ነዛ" ስር ተመ.

ንዛዥ "*ነዘዘ" ስር ተመ.

ንዝ "ናዘዘ" ስር "ኑዛዜ"ን ተመ.

ንዝህላል "እንዝህላል"ን ተመ.

ንዝረት "ነዘረ^{1}" ስር ተመ.

ንዝንዘኛ "ነዘነዘ" ስር ተመ.

ንዝንዝ ዝ.ከ.

ንዳድ^{1} "ነደደ^{1}" ስር ተመ.

ንዳድ^{2} ስ የሚያተኩስ፥ የሚያንቀጠቅጥና የሚያቃዥ የወባ በሽታ።

ንዳዳም ቅ ንዳድ ወይም ወባ ያለበት።

ንዴተኛ "ነደደ^{2}" ስር ተመ.

ንዴት ዝ.ከ.

ንድፈሃሳብ ስ የተለያዩ ነገሮችንና ክስተቶችን በማገናዘብ ስርአት ባለውና በተጠቃለለ መልክ የሚገልፅ ወይም የሚያብራራ በተግባር ያልተተረጎመ እውቀት።

ንድፍ^{1} "ነደፈ^{1}" ስር ተመ.

ንድፍ^{2} "ነደፈ^{2}" ስር ተመ.

ንድፍት ስ በቆላማ አገር ውስጥ የሚገኝ የጋማ ከብቶችን የሚያጠቃ የበሽታ አይነት።

ንጉር "ነጎረ" ስር ተመ.

ንጉር ቅቤ ዝ.ከ.

ንጉሳዊ "ነገሰ" ስር ተመ.

ንጉስ ዝ.ከ.

ንጋት "ነጋ" ስር ተመ.

ንግ "*ነጋ" ስር ተመ.

ንግረኛ (ንግርተኛ) "ነገረ" ስር ተመ.

ንግር(ንግርት) ዝ.ከ.

ንግስ "ነገሰ" ስር ተመ.

ንግስት ዝ.ከ.

ንግድ "ነገደ" ስር ተመ.

ንግግር "ነገረ" ስር ተመ.

ንጣሪ "ነጠረ^{1}" ስር ተመ.

ንጣት "ነጣ" ስር ተመ.

ንጣይ "ነጠለ" ስር ተመ.

ንጣፍ "*ነጠፈ" ስር ተመ.

ንጥል "ነጠለ" ስር ተመ.

ንጥር "ነጠረ^{1}" ስር ተመ.

ንጥሻ "*ነጠሰ" ስር "እንጥስታ"ን ተመ.

ንጥቂያ "ነጠቀ" ስር ተመ.

ንፁህ "ነፃ" ስር ተመ.

ንፅህና ዝ.ከ.

ንፅፅር "*ነፀረ" ስር ተመ.

ንፉግ "ነፈገ" ስር ተመ.

ንፊፊት "ንፍፊት"ን ተመ.

ንፉስ "ነፈሰ" ስር "ነፋስ"ን ተመ.

ንፉሽ "ነፈሰ" ስር ተመ.

ንፉው "ነፋ^{1}" ስር ተመ.

ንፌት(ንፊት) "ነፋ^{2}" ስር ተመ.

ንፍር ውሃ "ነፈረ"ስር ተመ.

ንፍርቅ "ነፈረቀ" ስር "ነፍረቅ"ን ተመ.

ንፍሮ "ነፈረ" ስር ተመ.

ንፍቅ [ቄስ፥ ዲያቆን] ቅ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ረዳት፥ የቅዳሴ ስነስርአት በሚካሄድበት ጊዜ በዋናነት ተሰይሞ ስርአቱን ከሚያከናውነው ቄስ ወይም ዲያቆን በተጨማሪ በእለቱ ስርአት ላይ የሁለተኛነቱን ቦታ ይዞ የሚቀድስ ዲያቆን ወይም ቄስ።

ንፉቅ እግር ስ እንደ ጋማ ከብት ድፍን ሳይሆን እንደ ላም፥ በግ፥ ፍየል፥...ስንጥቃት ያለው ሰኮና።

ንፍግት "ነፈገ" ስር ተመ.

ንፍጊያ ዝ.ከ.

ንፍጣም "*ነፈጠ"ስር ተመ.

ንፍጥ ዝ.ከ.

ንፍፊት(ንፊፊት) ስ 1. ፍርንትት፥ የበጀድና የጭን መጋጠሚያ፥ ጉያ። 2. በእግር ወይም በእጅ ጣት ላይ በሚያጋጥም ህመም ምክንያት በፍርንትት ወይም በብብት ውስጥ የሚሰማ የህመም ስሜት።

ኖ የ"ን" ፊደል ሳብእ ዘር።

ኖረ ግ 1. ቆየ፥ ተቀመጠ። *ዘጠና ዓመት በህይወት ኖረ።* 2. አለ፥ ተገኘ። *ሊቃው ለቤት ከኖረ ዛሬውኑ ልትወስደው ትችላለህ።*

መኖሪያ ቅ 1. የአንድ ነገር ቋሚ አድራሻ፥ መቀመጫ፥መገኛ፥ ማደሪያ (ቤት፥ ሰፈር፥አገር)። 2. መተዳደሪያ፥ የአመት ልብስ፥ የእለት ጉርስ ለማግኘት የሚሰማሩበት የተግባር አይነት።

የመኖሪያ ፈቃድ ስ አንድ ሰው በባእድ አገር ሲኖር በዚያ አገር ውስጥ ለመኖር የሚያስችለውና በሚመለከተው የመንግስት አካል የሚሰጥ ፈቃድ።

ነዋሪ (ኗሪ) ቅ 1. የቆየ፥ ተቀማጭ። *ሰውየው እዚህ ቦታ ነዋሪ ነበሩ።* 2. ቋሚነት፥ ዘላቂነት ያለው።

ኑሮ ስ 1. አንድ ሰው በእድሜ ዘመኑ

የሚያሳልፈው ህይወት። 2. ለህይወት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች የሚገኙበት ሁኔታ። 3.አኗኗር።

ኑሮ ኑሮዬ አለ ለቤቱ፣ ለቤተሰቡ፣ ለትዳሩ በማሰብ ጣረ፣ ጋረ፣ አጥብቆ ሰራ።

አኖረ ግ 1.አስቀመጠ። 2. አቆየ፣ አከረመ። 3. ረዳ፣ አስተዳደረ። *የሚያኖረኝ ላንቴ ነው።*

አኗኗር ስ የኑሮ ሁኔታ።

ኖራ ስ ከተቃጠለ በሃ ድንጋይ የሚገኝና ለግንባታ ስራ የሚያገለግል ነጭ ንጥረ ነገር።

ኖር "**ነወር**"ን ተመ.

-ኖሮ ተው.ግ. ትንቢታዊ ሃሳብ ጊዜን የሚገልፅ ቃል። *ብትመጣ ኖሮ በዓሉን አብረን እናከብር ነበር።*

***ኖቀኖቀ**

አኖቀኖቀ ግ አጉተመተመ፣ አጉረመረመ።

አኖቅኗቂ ቅ አጉረምራሚ፣ ነጭናጫ።

ኖታ ስ የተለያዩ የሙዚቃ ድምፀ ቃናዎችን ለመግለፅ የሚያስችል የሙዚቃ ዜማ ምልክት።

ኖት ስ ህጋዊነት ያለው የወረቀት ገንዘብ።

ኖክኗካ "***ነከነከ**" ስር "**ነክናካ**" ን ተመ.

ኗ የ"ን" ፊደል ፍንፅቅ ዘር።

ኗሪ "**ኖረ**" ስር "**ነዋሪ**"ን ተመ.

አ

አ ከ"ኘ" ፊደል ዘር ተከትሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል ግእዙ ሆሄ።

አረ 1.ለማጋነን የሚባል። *አረ ጉድ ፈላ!* 2.መገረምን ለመግለፅ የሚባል። *አረ! የሚገርም ነው።* 3.ለመጠየቅ ወይም ለማረጋገጥ የሚባል። *አረ? እውነትህን ነው?* 4.ለመለመን፡ እባክህ ለማለት ከሌላ ቃል ጋር በመጣመር የሚባል። *አረ እባክህ ስጠኝ።* 5.ምክር አዘል ማስጠንቀቂያ ለመስጠት ወይም አንድን ነገር በርትተህ፥ ጠንክረህ አድርግ ለማለት ከሌላ ቃል ጋር ተጣምሮ የሚባል። *አረ ተው ሂድ/ አረ አጥና።*

ኡ የ"አ" ፊደል ካእብ ዘር።

ኡሁ

ኡሁ አለ ግ ሳለ።

ኡኡ

ኡኡታ ስ ጩሀት፡ እሪታ።

ኡኡ አለ ግ እሪ አለ፡ ጮሀ።

ኡደት "**አወደ**²" ስር ተመ.

ኢ የ"አ" ፊደል ሳልስ ዘር።

ኢ— የአፍራሽነት ትርጉም ይዞ ከሌላ ቃል ጋር የሚገባ እስር ምእላድ። *ኢሳይንሳዊ /ኢሰብአዊ*።

ኢሳማ "**አሰመ**²" ስር ተመ.

ኢማማ ስ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች የሚያደርጉት የራስ ጥምጥም።

ኢማም ስ የእስልምና ሃይማኖት ምሁር፤ የፀሎት መሪ።

ኢምንት ስ 1.በጣም ትንሽ፤ ቅንጣት። 2. የተናቀ፡ ከቁጥር የማይገባ።

ኢምፔሪያሊዝም ስ ግዛት በማስፋፋትና በሌላው አገር ላይ ተፅእኖ በማድረግ ወይም አገሮችን በቅኝ ግዛትነት በመያዝ መርህ ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ እምነት።

ኢርቱእ ተሳቢ "**ርቱእ**" ስር ተመ.

ኢሰብአዊ "**ሰብ (ሰብእ)**" ስር ተመ.

ኢሳይንሳዊ "**ሳይንስ**" ስር ተመ.

ኢንሱሊን ስ ከእንስሳት ቆሽት የሚዘጋጅና ለስኳር ህሙማን የሚሰጥ መድሃኒት።

ኢንሳይክሎፒዲያ ስ በሁሉም የእውቀት ዘርፎች ወይም በአንድ በተወሰነ የሙያ መስክ ያሉ ፅንሰ ሃሳቦችን በፊደል ተራ መዝግቦ ሰፋ ባለ ሁኔታ አብራርቶ የሚገልፅ አንድ ወይም ከአንድ በላይ ጥራዞች ያሉት መፅሃፍ።

ኢንስቲትዩት ስ ተቋም።

ኢንሹ ስ መልኩ ከወደላይ ጠቆር ያለ ግራጫ ሆኖ ከወደሆዱ ነጭ የሆነ፡ ረጅምና ከወደጫፉ ቆልመም ያለ አፍንጫና ቀጭን አንገት ያለው፡ እሾሃማ ቁጥቋጦዎች ባሉበት ቆላማ ስፍራዎች የሚገኝ፥ ሳርና ቅጠላ ቅጠል የሚመገብ የዱር እንስሳ(ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።

ኢንሹራንስ ስ 1.መድን፤ በቋሚነት በየወሩ የተወሰነ ገንዘብ በማስከፈል ደንበኞቹ የሞት፥ የአካል መጉደል፡ የቤት ንብረት መዘረፍ፥ መቃጠል፥... ሲያጋጥማቸው በደንቡ መሰረት ገንዘብ በመክፈል ወይም የጠፋውን፥ የተበላሸውን ንብረት በመተካት አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት። 2. ከላይ በተራ ቁጥር አንድ በተጠቀሰው መሰረት ለደንበኛው ድርጅቱ የሚሰጠው ዋስትና ወይም አደጋው በአጋጠመው ጊዜ የሚሰጠው የገንዘብ ወይም የንብረት ክፍያ።

ኢንሹራንስ አለው ከኢንሹራንስ ወይም ከመድን ድርጅት የሚሰጠው ዋስትና አለው።

ኢንሹራንስ ገባ የኢንሹራንስ ወይም የመድን ድርጅት በሚሰጠው አገልግሎት ተጠቃሚ ለመሆን በየወሩ ክፍያ እየከፈለ ደንበኛ ሆነ።

ኢንቶ (እንቶ) ስ እንጉዳይ የሚመስልና ቁመቱ ከእንጉዳይ ከፍ የሚል፥ መልኩ ነጣ ያለና ተጠብሶ የሚበላ ተክል።

ኢንዱስትሪ ስ 1.የፋብሪካዎችና ትላልቅ የምርት ድርጅቶች አጠቃላይ መጠሪያ። 2. በአንድ አይነት ዘርፍ ብዙውን ጊዜ በርካታ ሰዎችን በማሳተፍና የማሽን መሳሪያዎችን በመጠቀም የሚካሄድ ስራ።

የኢንዱስትሪ ውጤት ስ ከኢንዱስትሪ የተገኘ ምርት።

ኢንጂነር ስ መሃንዲስ።

ኢኮኖሚ ስ 1.የአንድ ሃገር የተፈጥሮ ሃብት አያያዝና አጠቃቀም ስርአት። 2.ቁጠባ። ***ኑሮውን በኢኮኖሚ መምራት መቻል አለበት።***

የኢኮኖሚ ቀውስ ስ የስርአተ ኢኮኖሚ መዛባት።

ኢኮኖሚስት ስ በኢኮኖሚክስ ሳይንስ የሰለጠነ ባለሙያ።

ኢኮኖሚክስ ስ የአንድን አገር ሃብት አመራረትና አጠቃቀም የሚያጠና የማህበራዊ ሳይንስ ዘርፍ።

ኢኳቶር ስ በምድር ወገብ ላይ ያለ የሃሳብ መስመር፡ የምድር ሰቅ።

ኢየሱስ [ክርስቶስ] ስ መድሃኒት፥ አዳኝ፤ ከሦስቱ ስላሴዎች አንዱ የሆነው እግዚአብሄር ወልድ።

—ኢያ "—ያ"ን ተመ.

ኢዮቤልዩ ስ አንድን ትልቅ ድርጊት ወይም ሁኔታ ለማስታወስ በየሃያ አምስት ዓመት የሚከበር በዓል:: *የወርቅ ኢዮቤልዩ /የብር ኢዮቤልዩ::*

ኢዮሃ አበባዬ (እዮሃ አበባዬ) ስ የመስቀል ዋዜማ እለት ችቦ ሲያበሩ ወይም ችቦውን ይዘው ደመራውን ሲዞሩ የሚዘፍኑት ዘፈን::

ኢድ አል አድሃ ስ ነቢዩ ኢብራሂም ከአላህ በታዘዘው መሰረት ልጁን እስማኤልን ለመሰዋት ሲዘጋጅ በምትኩ ላይ ከሰማይ በግ ያወረደበትንና በጉ የታረደበትን ቀን ለማዘከር ሙስሊሞች በየአመቱ የሚያከብሩት የበአል ቀን፤ አረፋ::

ኢድ አልፈጥር ስ በሙስሊሞች ዘንድ የሚከበር የፆም ፍቺ በአል::

ኣ^1 **የ"ኣ"** ፊደል ራብእ ዘር::

ኣ^2

ኣ በል አፍህን ክፈት::

ኣ ኣለ አፉን ከፈተ::

ኣ- 1.አድራጊነትንና አደራራጊነትን ለመግለፅ ከሌላ ግስ ጋር የሚገባ እስር ምእላድ:: *ኣበላ/ ኣጠጣ/ ኣመጣ*: 2. በ"ኣ" ለማይጀምሩ ግሶች የሳቢ ዘር መነሻ:: *ኣበላል/ ኣጠጣጥ::*

ኣሁን ተው.ግ. 1.በዚሁ ቅፅበት:: 2.በዚህ ሰዓት፡ ጊዜ፥ ወቅት፤ ዘንድሮ:: 3.ከጥቂት ጊዜ በፊት:: *ሲጠብቅህ ቆይቶ ኣሁን ነው የሄደው*:: 4.ከጥቂት ጊዜ በኋላ:: *ትንሽ ጠብቃት፣ ኣሁን ትመጣለች*: 5.እስኪ:: *ኣሁን እንዲህ ማድረግ ለምንድን ነው?*

በኣሁን ጊዜ ተው.ግ. በዛሬው ጊዜ፥ በዘመን፥ ወቅት::

ኣሁኑኑ ተው.ግ. በዚሁ ሰዓት ውስጥ፥ ቶሎ፥ ወዲያው:: *ኣሁኑኑ እመለሳለሁ::*

ኣሁን በኣሁን ተው.ግ በዚሁ ሰዓት ውስጥ፥ በፍጥነት፥ ወዲያውኑ:: *ኣሁን በኣሁን ሰረቀው::*

ኣሁንስት (ኣሁን ሰታ) ተው.ግ ከጥቂት ቀናት በፊት::

ኣሁንም እንደገና፡ በድጋሚ::

ኣሁንም ቢሆን በዚህ ጊዜም፡ ወቅትም፥ ሁኔታም፡ ምክንያትም ቢሆን::

ከኣሁን ቀደም ተው.ግ. ከዚህ ቀደም፥ ከኣሁን በፊት::

ከኣሁን [ከ] ኣሁን ተው.ግ. በቅርብ ጊዜ፡ ትንሽ ቆይቶ፥ አሁን:: *ከኣሁን ኣሁን ይመጣል ብሎ ሲጠብቀው ቀረ::*

የኣሁን ጊዜ ስ (ሰዋ.) ድርጊቱ አሁን እየተከናወነ ያለ መሆኑን የሚገልፅ የግስ ቅርፅ::

ኣሂዶ "ሄደ" ስር ተመ.

ኣሃ! 1.ኣንድ ነገር ጠፍቶ ወይም ተረስቶ ቆይቶ በኋላ ሲገኝ ወይም ትዝ ሲል የሚባል:: 2.ኣንድን ነገር ኣሁን ተረዳሁት፤ ገባኝ ለማለት የሚያገለግል ኣባባል:: *ኣሃ! ለዚህ ነው ፊቱን ያጠቆረብኝ::*

ኣሃዝ ስ ቁጥር፥ የቁጥር ምልክት (1፥ 2፥ ወይም ፩፥ ፪፥...)::

ኣሃዱ ስ ኣንድ:: *ኣሃዱ ብሎ ስራውን የጀመረው በዚህ ወር ነው::*

ኣሄሄ (ሄሄ)! መገረምን፥ መደነቅን፥ ማዘንን፡ መቆጨትን፡ ዛቻን ለመግለፅ የሚነገር ኣባባል::

ኣህዛብ ስ ሃይማኖት የለሽ፡ በጣኦት የሚያመልክ ህዝብ::

ኣህያ ስ 1.በኣቋም ከፈረስና ከበቅሎ የሚያንስ፥ ለጭነት የሚያገለግል የጋማ ከብት:: ✚ 2. (ስድብ) ደደብ፥ የማይገባው(ለእሱን የቤት እንሳስ ስር ተመ.)::

የኣህያ ሆድ ሲመስል (ሰማይ) ሊነጋ ኣከበበ::

የኣህያ ኪንታሮት ስ 1.በፊንጢጣ ላይ የሚወጣ ቁስል:: 2. በውስጥ እግር ላይ የሚወጣና ለመርገጥ የሚያውክ ቁስል::

የኣህያ ውሃ ጠጪ የፈለገውን ነገር ቀስ ብሎ ሳይታወቅበት የሚያደርግ::

ኣህጉር ስ ክፍለ ኣለም::

ኣሆ ስ በሆታ ጊዜ ኣውራጁን ተከትለው ተቀባዮች የሚሉት የሆታ ዜማ::

ኣሆሌ "እኮሌ" ን ተመ.

ኣሆማ (ሆማ) ስ የዛፍ ኣይነት::

ኣለ ግ 1.ተናገረ:: 2.መልእክቱን፥ ሃሳቡን አስተላለፈ:: 3. መታ:: *በጥፊና በእርግጫ ኣለው::*

ማለት ስ የኣንድን ነገር ትርጉም፥ ምንነት ለማስረዳት ወይም ነገሩን ሲገልፁ ቆይቶ ሃሳብ ለመጠቅለልና ይበልጥ ለማብራራት ሲፈለግ የሚባል ቃል:: *ኣገር ማለት ህዝብ ነው/ለመወያየት ማለት ሃሳብ ለሃሳብ ለመለዋወጥ ...::*

ስትለው ለሶስተኛ ሰው እንዲተላለፍ የተፈለገን ነገር ለመልክተኛው እንዲህ ብለህ ንገረው ለማለት የሚባል ቃል:: *በቀለን ስትለው ገን ከቤትህ ልመጣለሁና ጠብቀኝ በለው::*

እንደምትለው ስትለው::

እንዳለ እንደፈለገ፥ እንዳዘዘ:: *እሱ እንዳለ ይደረጋል::*

በል (የ "ኣለ" ትእዛዝ ኣንቀፅ) 1.ተናገር:: 2.ኣድርግ፥ ፈፅም:: *በል ብላ / በል ሂድ::*

በለው 1.ንገረው፥ ኣሰማው:: 2.ምታው፥ ደብድበው::

በል ሲለው ሲያሰኘው::

በል በል አለው አሰኘው፤ ገፋፋው፤ አድርግ አድርግ የሚል ስሜት አነሳሳው።

ቢልልኝ ቢሆንልኝ፣ ቢሳካልኝ ኖሮ።

አልኩ ባይ የማይፈፅመውን ነገር ለመወደድ ቢል የሚያወራ።

ይሉታል ይጠራል፤ ይሰኛል፤ ይባላል። *ዝዝ ነው ይሉታል።*

ምን ይሉታል 1.ምን ተብሎ ይጠራል። 2.ስለ እሱ ምን እያሉ ያወራሉ።

ይሉኝታ ትዝብት፣ የሰው አስተያየት ፍራቻ፤ ምን ይሉኝ፣ ሰዎች ይተቹኛል፣ ይታዘቡኛል ብሎ ያለእውነተኛ ፍላጎት አንድን ነገር ከማድረግ መቆጠብ ወይም ለማድረግ መገደድ።

ይሉኝ አይደል ይሉኝታ ቢስ።

ይሉኝታ ቢስ ቅ ትዝብትን፣ ሃሜትን የማይፈራ፣ ይሉኝታ የሌለው።

ይበል ግሩም፣ ድንቅ ለማለት የሚባል ቃል (ብዙውን ጊዜ ለጥሩ ቅኔ ማወደሻ የሚሰነዘር ቃል)።

ተባለ ግ 1.ተነገረ፣ ተወራ። 2.ተሰየመ፣ ስም ተሰጠ። *የት/ቤቱ ስም የእውቀት ጮራ ተባለ።*

— **በመባል** — በመሰኘት ወይም —በሚል ስም። *ት/ቤቱ የእውቀት ጮራ በመባል የሚታወቅ ነው።*

የማይባል የማይነገር፣ መባል የማይገባው።

ይባላል ተብሎ ይጠራል።

አባባል ስ 1.አነጋገር። 2.የአነጋገር ፈሊጥ፣ ዘዬ።

አለ ግ 1.በህይወት ነው። *አልሞተም አለ።* 2.ይገኛል። *ምግብ አለ።* 3.ተገኘ፣ ኖረ። *ገንዘቤ ሳላለቀም ላለ/መብራቱ ጠፍቷል? ላይ አለ።* 4.የአንድ ነገር ባለቤት ወይም ባለ ይዞታ መሆንን ለማመልከት የሚያገለግል። *መፅሃፍ አለኝ።*

አለሁ አለሁ ባይ (ስድብ) 1.እዩኝ እዩኝ፣ ልታወቅ ልታወቅ ባይ። 2.አጎብዳጅ።

አለበት አንድ ነገር እንዲደረግ፣ እንዲፈፀም የግዴታ አስፈላጊ መሆኑን የሚገልፅ ቃል። *ወንጀለኛው ለፍርድ መቅረብ አለበት።*

ያለ የሌለ 1.እያለ፣ ብዙ። 2.በሙሉ። *ያለ የሌለ ንብረቱን ሸጠ።*

አለኝታ ስ መመኪያ።

እንዳለ 1.በሙሉ፣ በጠቅላላ፣ ምንም ሳይቀር። 2.ምንም ሳይነካለት፣ ቀደም ሲል የነበረበት ሁኔታ ሳይጓደል።

አለ—(ያለ—) 1.ሳይኖር፣ ከ-በስተቀር። *ያለገንዘብ እቃውን ማግኘት አይቻልም/ያለእሱ አይሆንም።* 2.አፍራሽ ምእላድ። *ያለመስራት ድህነትን ሊያስከትል ይችላል።*

አለበለዚያ (ያለበለዚያ፣ አለዚያ፣ ያለዚያ፣ አሊያ) ቀድሞ የተነገረው ነገር ካልሆነ (ይህ ካልሆነ) ለማለትና አማራጭ ለመስጠት የሚነገር። *ስራህን አክብር፣ አለበለዚያ ትቸገራለህ።*

አለለ^1 ግ አለሌ ሆነ።

አለል ዘለል አለ ስራ ፈታ፣ አውደለደለ፣ ዋልጌ ሆነ።

አለሌ ስ 1.ከፈረስ በቅሎን የሚያስወልድ፣ በቁመናውና በጥንካሬው ተመርጦ እየተቀለበ የሚቀመጥ አህያ። ቅ 2.(ስድብ) ቅንዝረኛ።

አለለ^2 ግ አቀለመ፣ ቀለም ነከረ።

አለላ ስ ቀለም የተነከረ በንደል ወይም አክርማ።

አለላ ሙዳይ ስ ከአለላ የተሰራ ትንሽ አገልግል ወይም ሙዳይ።

አለሌ "አለለ^1" ስር ተመ.

አለሎ "አሎሎ"ን ተመ.

አለመ^1 ግ ህልም አየ።

እልም "ህልም"ን ተመ.

አለመ^2 ግ 1.ተኩሶ ወይም ወርውሮ ለመምታት አነጣጠረ። 2.አቀደ፣ ተለመ፣ ነደፈ።

ኢላማ ስ በማነጣጠር ወርውሮ ወይም ተኩሶ የሚመታበት የተወሰነ ቦታ ወይም ምልክት።

አላማ ስ 1.ኢላማ። 2.እቅድ፣ ትልም። 3.ሰንደቅ አላማ።

አለመኛ "አለም" ስር ተመ.

አለመጠ ግ ሰነፈ፣ ቀለደ፣ አሾፈ፣ አላገጠ (በስራ ላይ)።

አልምጥ (አልማጭ) ቅ ልግመኛ፣ በስራ ላይ የሚያሾፍ።

አለም ስ መሬትና በመሬት ላይ ያሉ ህዝቦችና አገሮች በሙሉ።

አለሙን አየ 1.አገባ፣ ተዳረ፣ ትዳር መሰረተ። 2.ደስታ፣ በድሎት ኖረ።

አለም በቃኝ ስ 1.የእድሜ ልክ እስራት። 2.የእድሜ ልክ እስራት የተፈረደባቸው ሰዎች የሚታሰሩበት ቦታ።

አለም በቃኝ አለ መነነ።

አለም አቀፍ ቅ መላውን አለም ወይም በርካታ አገሮችን የሚመለከት፣ የሚያካትት፣ የሚያጠቃልል (ድርጅት፣ ስብሰባ፣ ...)።

የአለም ስም ስ የአንድ ሰው የክርስትና ስም ሳይሆን ዘወትር የሚጠራበት ስም።

የአለም ጦርነት ስ ብዙ የአለም አገሮች የተሳተፉበት ጦርነት (ለምሳሌ 1ኛና 2ኛ

የእስም ጦርነት)።

አለመኛ ቅ የደላው፣ የተመቸው።

አለማዊ ቅ 1.በምድር ላይ በህይወት ለሚቆይበት ጊዜ ብቻ የሚጨነቅ፣ ከሞት በኋላ ላለው ህይወት ግድ የሌለው። 2.መንፈሳዊ ያልሆነ፣ ስጋዊ።

አለቀ ግ 1.ተፈፀመ፣ ተጨረሰ። 2.ሞተ። *በአደጋው ብዙ ሰው አለቀ።* 3.አረጀ (ልብስ፣ ጫርቅ፣ ...)።

ማለቂያ ስ መጨረሻ፣ ማብቂያ።

አላቂ ቅ ለብዙ ጊዜ የማይቆይ ወይም የማያገለግል፣ በአጭር ጊዜ የሚያልቅ።

እላቂ ቅ 1.አገልግሎቱን የጨረሰ፣ ያረጀ (ልብስ)። 2.አገልግሎት ሰጥቶ ሊያልቅ ትንሽ የቀረው። *እላቂ ሳሙና።*

እልቂት (እልቀት) ስ በብዛት መሞት፣ ማለቅ።

ተላለቀ ግ ተጋደለ፣ ተፋጀ።

አለቃ ስ 1.ሹም፣ የበላይ፣ እዛዥ፣ ዋና። 2.(ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) የአንድ ቤተ ክርስቲያን ሹም ወይም አስተዳዳሪ።

አለቃና ምንዝር ሹምና ጭፍራ።

እልቅና (ልቅና) ስ አለቅነት።

አለቅት "አልቅት"ን ተመ.

አለበ¹ ግ 1.ሱትን በመሳብ ወተት አወጣ። 2.(ዘይ.) በዘበዘ፣ በጠበጠ። *ገንዘቡን አለበው።*

አለበ² ግ 1.አንዳጠረ፣ አለመ፣ አዘገበ። 2.ምልክት፣ እልባት አደረገ።

እልባት ስ 1.አንባቢ የሚፈልገውን ወይም ያቆመበትን ገፅ ለማወቅ እንዲረዳው በመፅሃፍ ውስጥ የሚያስቀምጠው ምልክት። 2.የነገር ማብቂያ፣ መደምደሚያ፣ መጨረሻ። *ጉዳዩ እልባት አገኘ።*

እልባት አደረገ ግ 1. አንባቢው የሚፈልገውን ወይም ያቆመበትን ገፅ ለማወቅ በመፅሃፍ ውስጥ ምልክት (ክር፣ ሳር፣ ...) አስቀመጠ። 2.ነገርን ወይም ጉዳይን ደመደመ፣ ፈፀመ፣ ቋጨ።

አለበለዚያ (አለዚያ፣ ያለበለዚያ፣ ያለዚያ) መ. ሊከተል የሚችል ውጤትን የሚገልፅ ሃሳብን ለማያያዝ የሚያገለግል አያያዥ ቃል። *መከላከያውን ውሰድ አለበለዚያ ትታመማለህ።*

-አለብላቢት "ለበለበ" ስር ተመ.

አለተለተ ግ በጣም ወፈረ (ሰውነት)።

አለት ስ በመሬት ላይ ወይም በወንዝ ውስጥ በተፈጥሮ ተነጥሮ የሚገኝ ጠንካራ ድንጋይ።

አለታም ቅ አለት የሚበዛበት ስፍራ።

አለንጋ ስ ከጠፍር ወይም ከጉማሬ ቆዳ፣... የሚሰራ መግረፊያ።

አለንጋ ጣት ስ ቀጠንና ረዘም ያለ የሚያምር የእጅ ጣት።

አለኝታ "አለ" ስር ተመ.

አለዚያ "አለበለዚያ"ን ተመ.

አለፈ ግ 1.ሃ.ደ. 2.ሞተ። *በመኪና አደጋ ህይወቱ አለፈ።* 3.ተወ፣ ዘለለ። *እኔን አልፎ አጠገቤ ላለው ሰው ሰጠ።* 4.ዋለ፣ ዋቢ ሆነ። *የጠየቁህን ገንዘብ አበድረው እኔ አልፍለታለሁ።* 5.ቀረ፣ ተተወ። *ባለፈ ነገር መናደድ አይጠቅምም።* 6.ከልክ፣ ከወሰኑ፣ ከመጠኑ በለጠ ወይም ጨመረ። *ወሰን አለፈ።* 7.ከአለበት ክፍልና ደረጃ ወደሚቀጥለው ክፍል ተዛወረ። *ወደ 5ኛ ክፍል አለፈ።* 8.ሾለከ፣ ወጣ። *ብርሃኑ በቀዳዳው አልፎ ገባ።* 9.ቀደመ፣ ወደ ኋላ ተወ። *እሱ ሲንቀረፈፍ እኔ አልፌው ሄድኩ።*

አለፈለት ከችግሩ ተላቀቀ፣ ቀን ወጣለት።

አለፈበት 1. ኋላ ቀር ሆነ፣ ፋሽኑ አበቃ። 2.ጊዜው ሄደበት፣ ሳይጠቀምበት ቀረ።

ያለፈበት ዘመናዊ ያልሆነ፣ ኋላቀር የሆነ። *ያለፈበት አለባበስ።*

ይለፍ (የይለፍ ወረቀት) ስ ወደ አንድ ቦታ ለመግባት ወይም ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለመሄድ ወይም ለመዘዋወር የሚሰጥ የፈቃድ ወረቀት።

ማለፊያ ስ 1.ጥሩ፣ ውብ፣ ደህና። ቅ 2.መተላለፊያ።

ሃላፊ (አላፊ) ቅ 1.ቋሚ ያልሆነ፣ ለዘላለም የማይኖር። *ገንዘብ ሃላፊ ጠፊ ነው።* ስ 2.ዋና፣ ባለቤት፣ አዛዥ። *የቢሮ ሃላፊው ማን ነው።*

አላፊ አግዳሚ ወጪ ወራጅ፣ ተመላላሽ መንገደኛ።

ሃላፊ ጊዜ ስ (ሰዋ.) ድርጊቱ የተከናወነ ወይም የተፈፀመ መሆኑን የሚገልፅ የግስ ቅርፅ (ለምሳሌ *ሞተ፣ ሄደ፣ ...*)።

ሃላፊነት (አላፊነት) ስ 1.ተያዥነት፣ ዋቢነት፣ ተጠያቂነት። *እቃው ቢጠፋ ሃላፊነቱን አልወስድም።* 2.ስልጣን። *ሃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር።*

ሃላፊነቱን አወረደ ዋቢነቱን፣ ተያዥነቱን አነሳ፣ ሰረዘ።

ሃላፊነቱን ወሰደ 1.አንድ ነገር ለማድረግ ወይም ለመፈፀም ግዴታ ውስጥ ገባ። 2.ስለ ጉዳዩ ተጠያቂው እኔ ነኝ አለ። *በድብቅ ጥቃት ያደረሰው ወገን ማንነቱን ገልፆ ስለድርጊቱ ሃላፊነቱን ወሰደ።*

ሃላፊነት የሚሰማው 1.ሃላፊነትን ወይም ግዴታን መወጣት ይችላል ተብሎ እምነት የሚጣልበት። 2.ግዴታውን የተገነዘበና በተግባር የሚተረጉም (ሰው)።

አለፊታ ስ 1.ትርፍ ነገር፤ ላፍ አላፊ። 2.ከተገቢው መጠን በላይ፤ አላፊ።

አላፊ ቅ 1.ላፍ አላፊ። 2.ከተወሰነው ልክ ወይም ገደብ በላይ የሆነ።

አልፈት (ህልፈት) ስ መሞት፤ ከዚህ አለም በሞት መለየት።

ህልፈተ አለም ስ የአለም ፍፃሜ ወይም መጨረሻ።

ተላለፈ ግ 1.ከአንዱ ወደ ሌላ ተራመደ፤ ተዛመተ፤ ተጋባ (በሽታ)። 2.ጣሰ፤ አፈረሰ (ህግን)። 3.ተዛወረ፤ ተሸጋገረ፤ለሌላ ጊዜ እንዲሆን ተወሰነ። 4.ሄደ፤ አለፈ። *በዚያ በኩል ሲተላለፍ ላየው ነበር።* 5.ከአንዱ ወደ ሌላው ተሻገረ፤ አለፈ፤ ሲወርድ ሲዋረድ መጣ፤ ተወረሰ። *ከትውልድ ትውልድ ተላለፈ።* 6.እያንዳንዱ ወደየተቃራኒው አቅጣጫ ሄደ፤ ተጠላለፈ። *ተላልፎ ተቆለፈ።* 7.ተሰራጨ፤ ተነገረ። *አዲስ መመሪያ ተላለፈ።* 8.ሳይገናኝ ቀረ።

መተላለፊያ ስ መሄጃ፤ መሹለኪያ፤ ማለፊያ (በር፤ መንገድ፤ ...)።

ተላላፊ ቅ 1.ወጭ ወራጅ፤ መንገደኛ። 2.በግራና በቀኝ ያለውን የልብሱን ክፍል፤ አንዱን በአንዱ ላይ በማሳለፍ የሚቆለፍ (ኮት፤ ቀሚስ፤ ...)።

ተላላፊ በሽታ ስ በንክኪ፤ በትንፋሽ፤ በዝንብ ወዘተ. ምክንያት ከአንዱ ወደሌላ የሚጋባ ወይም የሚዛመት በሽታ።

አሳለፈ ግ 1.በጊዜው ወይም በወቅቱ ሳይደርስ ቀረ፤ ዘገየ። *የስራ ሰዓት አሳለፈ።* 2.አደለ፤ አስተናገደ፤ አቀረበ። *ጠጅ ያሳልፋል።* 3.ተወ፤ ማረ፤ ታገሰ፤ ይቅርታ አደረገ። *የዛሬውን አሳልፌሃለሁ።* 4.ከችግር አላቀቀ፤ ቀን አወጣ። *ወንድሙ ነው ያሳለፈለት።* 5.መንገድ ለቀቀ። *አሳልፈው! ሊሄድ ቸኩሏል።* 6.ነፍስ አጠፋ፤ ገደለ። *ህይወቱን በገዛ እጁ አሳለፈ።* 7.አሾለከ፤ አስገባ። *እግሩን በወንበር ስር አሳልፎ ረገጠኝ።*

አሳልፎ ሰጠ ለባለጋራ ወይም ለጥቃት ዳረገ፤ አጋለጠ።

አሳላፊ ስ በድግስ ወይም በግብዣ ላይ የሚያስተናግድ፤ ቋሚ።

አስተላለፈ ግ 1.አዘዋወረ፤ ለሌላ ጊዜ ቀየረ። *ስብሰባውን ለሌላ ጊዜ አስተላለፉት።* 2.አዛመተ፤ አጋባ (ተላላፊ በሽታን)። 3.አወሳሰበ፤ አመሳቀለ። 4.አሰራጨ፤ ነገረ (በዜና ማሰራጫ፤ በፅሁፍ፤...)። 5.በውስጡ እንዲያልፍ አደረገ (ኮረንቲን፤ ድምፅን፤ ብርሃንን፤ ...)። 6.ላከ፤ ሰጠ፤ ወሰደ። *ወደ ወህኒ ቤት አስተላለፉት።* 7.አወረሰ።

አሉባልታ ስ ያልተረጋገጠ ወሬ፤ ሃሜት።

አሉባልተኛ ቅ (ስድብ) የአሉባልታ ወሬን የሚያዘምት ወይም የሚያወራ።

አሉታ ስ አሌ ማለት ወይም እብለት፤ የአዎንታ ተቃራኒ።

አሉተኛ ዋሾ።

አላህ ስ (እስል.) ፈጣሪ፤ አምላክ፤ እግዚአብሄር።

አላል ስ በጋማ ከብት ጭነት ላይ ተጣማሪ ሆኖ የሚደረብ ትንሽ ጭነት።

አላማ "አለመ^{2}" ስር ተመ.

አላቂ "አለቀ" ስር ተመ.

አላባ ስ 1.የእህል ወይም ከመሬት የሚገኝ የማንኛውም ነገር ምርት። 2.የስራ ውጤት ወይም ፍሬ።

አላዘነ ግ 1.ለቅሶ በሚመስል ድምፅ ጮሀ፤ አንቋረረ (በተለይ ውሻ)። 2.ስለአንድ ጉዳይ ደግሞ ደጋግሞ አወራ፤ ቸከ አለ።

አላድ ስ የብር አኩሌታ የነበረ ገንዘብ፤ ሃምሳ ሳንቲም።

አሌ

አሌ አለ ግ አበለ፤ ካደ።

አሌጠ ግ አፌዘ፤ ላገጠ።

አል— (በሚያስር ጊዜ "ም"ን ይጨምራል) አፍራሽ ሃሳብ መመስረቻ ምእላድ። (ለምሳሌ *ሰራ→አልሰራም/ በላ→አልበላም*)።

አልሚ ምግብ "ለማ" ስር ተመ.

አልማዝ ስ 1.ከንፁህ ካርቦን የሚገኝና በጥንካሬው የሚታወቅ ብሩህ የሆነ የከበረ ድንጋይ። 2.ከአልማዝ የተሰራ ጌጥ።

አልምጥ "አለመጠ" ስር ተመ.

አልቃሽ ስ አልሄድ ያለን በሬ፤ አህያ፤... እንዲሄድ ወይም ፍጥነት እንዲጨምር የሚያደርግ ሹልነት ያለው መንጎጫ፤ መጎንተያ እንጨት ወይም ብረት።

አልቅት (አለቅት) ስ በውሃ ውስጥ የሚኖርና ከብቶች ውሃ ሲጠጡ በአፋቸው ገብቶ ጉሮሮአቸው ውስጥ በመቀመጥ ደም የሚመጥ ትል መሳይ ነፍሳት።

አልቢትር "አርቢትር"ን ተመ.

—አልባ ቅ —የሌለው። *ስርአት አልባ።*

አልባሌ ቅ 1.የማይረባ፤ የማይታወቅ። *አልባሌ ቦታ አትዋል።* 2. ተራ፤ ተርታ። *ምስጢሩን ያወጣው አንድ አልባሌ ሰው ነው።*

አልባብ ስ ሲጨስ ጥሩ ሽታ ያለው የጭስ

እንጨት።

አልቤርጎ (ቤርጎ) ስ እንግዶች ለማረፊያነት የሚከራዩት የሆቴል ቤት ክፍል ወይም መኝታ ቤት።

አልቤን ስ የጠመንጃ አይነት።

— **አልቦ** ቅ — የሌለው።

አልቦ ስ ከወርቅ ወይም ከብር የሚሰራና ሴቶች በእግራቸው ላይ የሚያደርጉት ጌጥ።

አልቴት ስ እንደ ራስ ምታት ያለን በሽታ ያድናል ተብሎ የሚሸተት እንደ ሙጫ ያለ ነገር።

አልኮል ስ 1.እንደ ቢራ፣ ጂን፣ ውስኪ፣ ... ባሉ መጠጦች ውስጥ የሚገኝ አስካሪ ንጥረ ነገር። 2.በቀላሉ ተኖ ወደ ጋዝነት ሊቀየርና በቀላሉ በእሳት ሊቀጣጠል የሚችል፣ በሆስፒታል ውስጥ ለቁስል መጥረጊያና ለተለያዩ ተግባራት የሚያገለግል ፈሳሽነት ያለው ንጥረ ነገር።

አልኮል መጠጥ ስ በውስጡ ያለው የአልኮል መጠን ከፍተኛ የሆነ እንደ ጂን፣ ብራንዲ፣ አረቄ፣... ያለ የመጠጥ አይነት።

አልጀብራ ስ በፊደላትና በምልክት ጭምር የሚጠቀም የሂሳብ ትምህርት ዘርፍ።

አልጉም "**ለጎመ**" ስር ተመ.

አልጋ ስ 1.በላዩ ላይ ለመተኛት እንዲያመች ተደርጎ ከእንጨት ወይም ከብረት፣ ... የሚሰራ ባለአራት እግር መተኛ። 2.ዙፋን።

አልጋ ለዩ ለየብቻ ተኙ (ባልና ሚስት)።

አልጋ ላይ ዋለ ከህመም የተነሳ የአልጋ ቁራኛ ሆነ፣ ታመመ።

አልጋ በአልጋ ቀና፣ ምቹ (ለመንገድ)።

አልጋ ነቀነቀ ሸፈተ፣ አመፀ፣ ንጉስን ተቃወመ።

አልጋ ያዘ 1.አልቤርጎ ተከራየ። 2.የአልጋ ቁራኛ ሆነ፣ ታሞ ተኛ።

አልጋ ፈረሰ ንጉሱ ከስልጣን በመወገዱ አገሩ መሪ አልባ ሆነ።

ከአልጋ ወደቀ በህማማት ጊዜ የግብረ ስጋ ግንኙነት ፈፀመ።

[የ]አልጋ ልብስ ስ አልጋን ለማስጌጥ ከብርድ ልብስ በላይ የሚነጠፍ የአልጋ መሸፈኛ።

አልጋ አንጣፊ ስ በሆቴል ቤት ውስጥ አልጋ በማንጠፍ ስራ ላይ የተሰማራ ሰው።

አልጋ ወራሽ ስ በሞት ወይም በሌላ ምክንያት ንጉስ ዙፋኑን በሚለቅበት ጊዜ ንጉሱን ተክቶ መንገስ የሚችል የንጉስ ልጅ ወይም ወገን።

የአልጋ ቁራኛ ቅ ለረጅም ጊዜ በመታመሙ ምክንያት ከአልጋ የማይነሳ በሽተኛ።

አልጌ ስ በረጋ ውሃ ላይ ተንሳፎ የሚገኝና አረንጓዴ ቀለም ያለው ለስላሳ የእፅዋት አይነት።

አልጫ ስ 1.በእርድ ወይም ያለእርድ የተሰራ በርበሬ የሌለው ወጥ። ቅ 2.(ስድብ) ከስታራ ያልሆነ፣ ልፍስፍስ። *የወንድ አልጫ።*

አሎሎ (አለሎ) ስ እንደ ቅመማ ቅመም ያሉ ነገሮችን ለመቀጥቀጥ፣ ለመደፍጠጥ፣ ... የሚያገለግል ድብልብልና ከባድ የሆነ ድንጋይ።

አሎሎ ውርወራ ስ (ስፖ.) የብረት አሎሎን አርቆ ለመወርወር የሚደረግ ውድድር።

አመሃኘ "**መከነ**" ስር "**አመካኘ**"ን ተመ.

አመሰ ግ ከመቆየት የተነሳ ሽታው ወይም ጣእሙ ተበላሸ፣ እምክ እምክ አለ (ጥራጥሬ፣ ዱቄት)።

አማሳ ቅ ከመቆየት የተነሳ፣ ሽታው ወይም ጣእሙ የተበላሸ፣ እምክ እምክ የሚል (ጥራጥሬ፣ ዱቄት)።

አመለመለ ግ የተነደፈን ጥጥ በትንሽ በትንሹ በመሸብለል ወይም በመጠቅለል ለፈትል አዘጋጀ።

አመልማሎ ስ ተነድፎ በትንሽ በትንሹ የተሸበለለ ወይም የተጠቀለለና ለፈትል የተዘጋጀ ጥጥ።

አመለኛ "**አመል**" ስር ተመ.

አመለጠ ግ 1.እስረኛ ወይም በቁጥጥር ስር ያለ ወንጀለኛ ከእስሩ ወይም ከቁጥጥሩ ራሱን በህገወጥ መንገድ ነፃ አደረገ፣ ተሰወረ። *እስረኛው አመለጠ።* 2.ጥፋት፣ ወንጀል፣... ሰርቶ ሳይያዝ ወይም ሳይደረስበት ሸሸ፣ ተሰወረ። *ሌባው ሰርቆ አመለጠ።* 3.ተረፈ፣ ዳነ። *ከሞት አመለጠ።* 4.በድንገት ወይም ሳይታሰብ ወደቀ (እቃ)፣ አፈተለከ፣ ወጣ (ወሬ፣ ምስጢር፣ ሽንት፣ ...)። 5.በወቅቱ ወይም በጊዜው በአንድ የተወሰነ ቦታ ላይ ካለመገኘት የተነሳ ተፈላጊው ነገር ሳይገኝ ወይም ሳይደረስበት ቀረ። *አርፍዶ በመሄዱ ባቡሩ አመለጠው።*

ማምለጫ ስ መዳኛ፣ መትረፊያ (መንገድ፣ ዘዴ፣ ብልሃት ወይም ቦታ)።

አመል ስ 1.ባህርይ፣ ልማድ፣ ጠባይ። 2.ሱስ፣ ሃራራ። *የሲጋራ አመል አለበት።*

ለአመል (ላመል) 1.ለልማድ። *ሌባ ለአመሉ ዳቦ ይልሳል።* 2.ትንሽ ወይም ጥቂት። *ጨው አታብዢ፣ ለአመል ያህል ብቻ ጨምሪበት።*

አመል ነሳው እንዲነጫነጭ፣ ጠባዩን አበላሸው።

አመል አወጣ 1.መጥፎ ጠባይ አመጣ። 2.ደህና የነበረው ደበላሸ ጀመረ (እ.ቀ)።

አመለ ልስልስ ቅ ጥሩ ጠባይ ያለው፡ የማያስቸግር።

አመለ ቢስ ቅ ጥሩ ጠባይ የሌለው፡ ነጭናጫ።

አመለ ናጫ ቅ ዉቅሜቃ፡ አመለቢስ።

አመለ ወርቅ ቅ ጥሩ ጠባይ ያለው።

አመለ ድሃ ቅ ጥሩ ጠባይ የሌለው፡ ነጭናጫ፡ ከሰው የማይስማማ።

አመለ ጌታ ቅ ጥሩ ጠባይ ያለው።

አመለኛ ቅ 1.ልማደኛ። 2.መጥፎ ጠባይ ወይም ባህርይ ያለው፡ አስቸጋሪ።

አመልማሎ "**አመለመለ**" ስር ተመ.

አመመ^{1} ግ የጤና ማጣት ስሜት ተሰማ።

ህመም በፊደል ተራው ተመ.

ህመምተኛ "**ህመም**" ስር ተመ.

ህሙማን ብ.ከ.

ታመመ ግ ህመምተኛ ሆነ፡ ጤና አጣ፡ በሽተኛ ሆነ።

ታማሚ ቅ ህመምተኛ፡ በሽተኛ።

አሳመመ ግ የህመም ስሜት እንዲሰማ አደረገ።

አስታመመ ግ 1.ለበሽተኛ የሚፈለገውን ነገር በማድረግ ረዳ፡ ተንከባከበ። 2.ታገሰ፡ ቻለ፡ አባበለ። 3.ቀስ አድርጎ ያዘ፡ በጥንቃቄ ተጠቀመ። *ኢቃው ወርሶ ከጥቅም ውጭ እንዳይሆንብን እያስታመምኩ ነው የምገለገልበት።*

አመመ^{2} ግ በመደዳ በአንድ ጊዜ ሊሰራ የሚችለውን ስራ ገምቶና መድቦ መስራት ጀመረ (ለአጨዳ፡ ለአረም፡ ለቁፋሮ)።

እመም ስ በአንድ ጊዜ በመደዳ የሚከናወን ስራ (አጨዳ፡ አረም፡ ቁፋሮ)።

አመረቃ ግ አረካ፡ አስደሰተ።

አመርቂ ቅ በጣም ጥሩ የሆነ፡ የሚያረካ። *አመርቂ ውጤት ተገኝቷል።*

አመራር ስ በደጋ አካባቢ የሚበቅል፡ ቅጠሉ እንደቀጋው ሰፋ ሰፋ ያለና ሲቀምሱት የሚመር፡ መጠኑ ከግራዋ የማይበልጥ የእፅዋት አይነት።

አመሰ ግ 1.ጥራጥሬን፡ ዱቄትን፡ ... በሰማ ምጣድ ላይ በመጠኑ ሞቅ ሞቅ አደረገ። 2.አወከ፡ በጠበጠ፡ ረበሸ፡ አተራመሰ።

እምስ ስ በጣም ሳይበስል በምጣድ ላይ ሞቅ ሞቅ የተደረገ ጥራጥሬ፡ ዱቄት፡ ...።

አመሰሳሳ ስ የየወሩ የመጨረሻ ቀን። *ለመስከረም አመሰሳሳ ለገናኝ።*

አመሰኳ ግ አመነዠከ።

አመቀ ግ 1.አንድን ነገር በብዛት እቃ ውስጥ በመጠቅጠቅ ከተተ፡ ወመረ፣ አጨቀ። 2.ደብቆ ያዘ፡ ቻለ (ምስጢርን፡ ወሬን፡ ስሜትን)።

እምቅ ቅ የታመቀ፡ የታጨቀ።

አመቀመቀ ግ አመነታ፡ ወላወለ፡ አቅማማ።

አመት ስ 1.አስራ ሁለት ወሮች ወይም ሶስት መቶ ስልሳ አምስት ቀኖች ወይም ደግሞ በየአራት አመት አንድ ጊዜ ሶስት መቶ ስልሳ ስድስት ቀኖች ያሉት የጊዜ መጠን። 2.ዘመን፡ ጊዜ።

አመት አመት ድገመን ከአመት አመት አድርሰን (በዚሁን ጊዜ የአዲስ አመት እሸት ሲቀመስ የሚባል)።

አመተ ምህረት ስ ከክርስቶስ ልደት ወዲህ ያለው ዘመን መጠሪያ።

አመተ አለም ስ 1.አለም ከተፈጠረችበት ጊዜ ጀምሮ ያለው ዘመን። 2.ከክርስቶስ ልደት በፊት ያለው ዘመን መጠሪያ።

አመት በአል ስ አውደ አመት፡ በየአመቱ የሚከበር በአል (ገና፡ እንቁጣጣሽ፡ ጥምቀት፡ ፋሲካ፡ ...)።

አመነ ግ 1.ያለጥርጥር ተቀበለ፡ ተስማማ። 2.ማድረጉን ወይም መፈፀሙን ተቀበለ፡ አረጋገጠ። *መግደሉን አመነ።* 3.ታዘዘ፡ ገበረ፡ ተገዛ። *ሽፍቶቹ ለንጉሱ አምነው ገቡ።* 4.አመለከ። *በእግዚአብሄር ያመነ ይድናል።* 5.እምነት ጣለ።

ምእመን (ብ.ቁ. **ምእመናን**) ስ አማኝ (አማኞች)።

አማኝ ቅ 1.የአንድ ሃይማኖት ተከታይ። 2.የሚከተለውን ሃይማኖት አጥብቆ የያዘ።

እሙን ቅ 1.ታማኝ፡ የታመነ (ሰው)። 2.የታመነ፡ እውነት ነገር። *በድርቁ ብዙ ሰው መጎዳቱ እሙን ነው።*

እማኝ ስ አንድ ድርጊት ሲፈፀም የነበረ ወይም ያየ ወይም የሰማ ሰው፡ ምስክር።

እምነት ስ 1.ሃይማኖት፡ አምልኮ። 2.እርግጠኝነት። 3.ሃላፊነት፡ ታማኝነት። *እምነት የሚጣልበት ሰው አይደለም።*

እምነት አጎደለ እንዲጠብቅ፡ እንዲይዝ የተደረገውን አጠፋ፡ አበከነ፡ ሃላፊነቱን ሳይወጣ ቀረ።

እምነት ጣለ አመነ፡ ተመካ፡ እርግጠኛ ሆነ።

የእምነት ክህደት ቃል ስ የተወነጀሉበትን ወይም የተከሰሱበትን ነገር ማመን ወይም አለማመን፡ አድርጌያለሁ ወይም አላደረግሁም

በማለት የሚሰጥ የአወንታ ወይም የእሉታ ቃል። *የእምነት ክህደት ቃሉን ሰጠ።*

እምነተ ቢስ ቅ እምነት የማይጣልበት፣ ከሃዲ።

ታመነ ግ እምነት ተጣለበት።

ታማኝ (ተአማኒ) ቅ የሚታመን፣ እውነተኛ፣ ሃቀኛ፣ የማይጠረጠር፣ ከሃዲ ያልሆነ።

ተማመነ ግ 1.ተመካ። *በጉልበቱ ተማመነ።* 2.እርግጠኛ ሆነ። *በችሎታው ይተማመናል።*

ተማመኑ ግ ተካክደው በነበረው ጉዳይ ላይ ሃቁን አረጋግጠው በመቀበል ተስማሙ።

መተማመኛ ስ ማስረጃ፣ ማረጋገጫ፣ ዋስትና።

አሳመነ ግ 1. እንዲያምን አደረገ። 2.(በማስረዳት ወይም በመግለፅ) አንድ ሃሳብ ተቀባይነት እንዲኖረው አደረገ።

አሳማኝ ቅ ትክክለኛ፣ እውነተኛ፣ ተገቢ፣ ... ነው በማለት የሚቀበሉት (ሃሳብ፣ ነገር)።

አስተማመነ ግ እርግጠኛ፣ የማያጠራጥር ሆነ።

አስተማማኝ ቅ እርግጠኛ፣ የማያጠራጥር።

አመነታ (አመናታ) ግ ሳድርግ ላሳድርግ አለ፣ ሃሳቡ ለሁለት ተከፈለ፣ አወላወለ።

አመነዘረ ግ ከጋብቻ ውጪ የግብረ ስጋ ግንኙነት አደረገ፣ ዝሙት ፈፀመ።

አመንዝራ ቅ ከጋብቻ ውጪ የግብረ ስጋ ግንኙነት የሚያደርግ፣ ዝሙት የሚፈፅም (ሰው)።

አመነዠከ ግ እንደ በሬ፣ በግ፣ ... ያለ እንስሳ በደንብ ሳያደቅ የዋጠውን ከሆዱ እያወጣ እንደገና በማኘክ አደቀቀ፣ አመሰኳ።

ምንዣህ ስ ከብቶች ያመሰኩት ወይም ያመነዠኩት (መኖ)።

አመንዝራ "አመነዘረ" ስር ተመ.

አመክሮ "መከረ" ስር ተመ.

አመድ ስ አንድ ነገር በእሳት ሲቃጠልና እሳቱም ከጠፋ በኋላ የሚቀረው እንደ ዱቄት ያለ ነጣ ያለ ነገር።

አመዱ ቡን አለ በጣም ደነገጠ፣ ከው አለ።

አመድ ነፋበት አመድ መሰለ፣ ወዝ አጣ (ሰውነት)።

አመድ አደረገ ጨርሶ አወደመ፣ እልም አደረገ፣ አጠፋ።

አመዳም ቅ (ስድብ) 1.ወዝ የሌለው፣ ነጫጭብ። 2.ድሃ፣ ያጣ የነጣ።

አመዳይ ስ አመድማ መልክ ያለው ውርጭ።

አመድማ ቅ አመድ የሚመስል፣ ግራጫ መልክ ያለው።

አመፀ (አመጠ) ግ 1.ከዳ፣ ሸፈተ። 2.አስቸገረ፣ እምቢ አለ፣ አወከ።

አመፅ ስ 1.ሁከት፣ ረብሻ። 2.የተቃውሞ እንቅስቃሴ።

አመፀኛ (አመጠኛ) ቅ ረባሽ፣ በጥባጭ፣ ፀጥታ አደፍራሽ።

አሳመፀ ግ አመፅ አስነሳ፣ አሳደመ።

አሚና (ሃሚና) ስ የ"ሳሊበሳ"ን 1ኛ ፍቺ ተመ.

አሚን

የአሚን ሚስት ወይም ባል የመጀመሪያ ሚስት ወይም ባል።

አማ ግ አንድን ሰው በሌለበት በጥፋቱም ሆነ ያለጥፋቱ በክፉ አነሳ፣ ነቀፈ።

ሃሜት (አሜት፣ ሃሜታ፣ አሜታ) ስ 1.አንድን ሰው በሌለበት በመጥፎ ማንሳት። 2.አንድን ጉዳይ በማስመልከት የተነገረ ያልተረጋገጠ ወሬ። *የመንግስት ገንዘብ አጉድሏል የሚል ሃሜት አለ።*

ሃሜተኛ (አሜተኛ) ቅ በአጠገቡ የሌለን ሰው በመጥፎ የማንሳት ልማድ ያለው (ሰው)።

ታማ ግ አንድ የሆነ ነገር አድርጓል ወይም ፈፅሟል ተብሎ በመጠርጠር ወሬ ተወራበት።

አሳማ ግ እንዲታማ አደረገ፣ ምክንያት ሆነ።

አማሳ "አመሰ" ስር ተመ.

አማረ ግ 1.ተዋበ፣ ቆነጀ። 2.ውል አለ ወይም አበጀ። *ስጋ አማረኝ።* 3.ሰመረ፣ ጥሩ ሆነ። *የዘንድሮው አዝመራ አምሯል።*

አምሮት ስ ፍላጎት፣ ምኞት።

አምሮቱን ቆረጠ ያማረውን ነገር አግኝቶ ረካ።

አምሮቱን ተወጣ የሚፈልገውን ነገር አግኝቶ ወይም አድርጎ ረካ።

አማራት ስ 1.ቀጭን ድምፅ የምትሰጠውና በግራ እጅ በኩል የምትሆነው የከበሮ ቂጥ። 2.አረሆ። 3.ቀጭን ድምፅ ከሚሰጡት ከሰስቱ የበገና አውታሮች አንዱ።

አማተበ ግ በመስቀል ወይም ሁለት ጣቶቹን በማነባበርና የመስቀል ቅርፅ በመስራት ግንባሩን፣ ደረቱንና ትከሻዎቹን መጀመሪያ ግራውን ቀጥሎ ቀኙን በመንካት የመስቀል ምልክት ሰራ፣ አደረገ (በፀሎት፣ በመሳለም ጊዜ)።

አማት ስ 1.የባል ወይም የሚስት እናት ወይም አባት። 2.የባል እናት።

አማምቻ ስ እህትን ከዳሩ በኋላ አማች

የሆነውን ሰው እህት በማግባት የሚመሰረት የጋብቻ ትስስር።

አማች ስ የእህት ወይም የልጅ ወይም የዘመድ ባል።

ያማች ዳኛ ስ ጨካኝ ወይም ክፉ አማች።

አምቻ ስ አማችነት፡ በጋብቻ መተሳሰር።

አምቻ ጋብቻ ስ የጋብቻ ዝምድና።

አማን ስ ሰላም። *በአማን ቆመለን*።

አማኝ "**አመነ**" ስር ተመ.

አማጋ ስ ከመኖሪያ ቤት አካባቢ ርቆ የሚገኝ የከብቶች ማደሪያ ወይም በረት።

አሜራ ስ ቀለሙ ለመኑትሽ የሚሆን የእፅዋት አይነት።

አሜባ ስ 1.ያለ ማይክሮስኮፕ በአይን ብቻ ሊታይ የማይችልና በአፈር፡ በውሃ ወይም በሰውና በእንስሳት አካል ውስጥ ተገኞ ሆኖ የሚኖር ባለአንድ ህዋስ ነፍሳት። 2.በአሜባ ምክንያት የሚመጣ የተቅማጥ በሽታ።

አሜተኛ "**አማ**" ስር "**ሃሜተኛ**"ን ተመ.

አሜታ "**አማ**" ስር "**ሃሜት**"ን ተመ.

አሜት ዝ.ከ.

አሜን ስ እሺ፡ ይሁን፡ ይደረግ ለማለት በፀሎትና በምርቃት ላይ የሚባል ቃል።

አሜን ብሎ ተቀበለ እሺ ብሎ ተቀበለ።

አሜከላ ስ 1.በቆላና በወይና ደጋ የሚበቅል፡ እንጓው አጠር ያለና ጭንቅላቱ እንደ ኳስ የተድበለበለ የእሾህ አይነት። 2.(ዘይ.) ምቀኛ፡ ሰላም የማይሰጥ ባላጋራ።

—**አም** ቅ ←በብዛት ያለበት፡ ያለው ወይም መጠኑ ከሌላው ከፍ ያለ ነው ለማለት የሚያገለግል ምእላድ። *ብርዳም /አክስም/ ወተታም/ ጭንቅላታም*።

አምላክ "**መለከ**" ስር ተመ.

አምልኮ ዝ.ከ.

አምልከኛ ግ.ከ.

አምሮት "**አማረ**" ስር ተመ.

አምሳ (ሃምሳ) ስ 1.በአርባ ዘጠኝና በሃምሳ አንድ መካከል ያለ ቁጥር መጠሪያ፤ በአሃዝ ሲፃፍ ፶ ፡ '50' ነው። ቅ 2.በአርባ ዘጠኝና በሃምሳ አንድ መካከል ያለ ብዛትን የሚያሳይ። *ሃምሳ ልጆች*።

አምሳ (ሃምሳ) አለቃ ስ ከአስር አለቅነት ቀጥሎ ያለ ወታደራዊ ማእረግ ስም።

አምሳ (ሃምሳ) እግር ስ ብዙ እግሮች ያሉት፡ በክረምት ጊዜ የሚፈጠር ወይም የሚታይ ትል።

አምሳ (ሃምሳ) እግር

አምሳል "**መሰለ**" ስር ተመ.

አምሳያ ግ.ከ.

አምስት ስ 1.በአራትና በስድስት መካከል ያለ ቁጥር መጠሪያ፤ በአሃዝ ሲፃፍ '፭'፥ '5' ነው። ቅ 2.በአራትና በስድስት መካከል ያለ ብዛትን የሚያሳይ ። *አምስት ጣቶች*።

አምበል (አንበል) ስ 1.መሪ፡ አለቃ፡ አበጋዝ፡ አዝማች። *የጦር አምበል*። 2.የእግር ኳስ፡ የመረብ ኳስ፡ ... ጨዋታ የቡድን ተጠሪ ወይም መሪ።

አምበልጋ ቅ ፈሪ፡ ቡከን።

አምበሬ ጭቃ ስ ለግንብ የሚያገለግልና ፈሳሽ ያልሆነ የጭቃ አይነት።

አምበሳ "**አንበሳ**"ን ተመ.

አምቡላ (አንቡላ) ስ የጠጅ አተላ።

አምቡላንስ ስ ድንገተኛ ህመም ወይም አደጋ ያጋጠማቸውን ወይም በጦር ሜዳ ላይ ጉዳት የደረሰባቸውን ሰዎች እርዳታ ወደሚያገኙበት (ክሊኒክ፡ ሆስፒታል፡...) የሚያጓጉዝ መኪና።

አምባ ስ 1.በአንድ አካባቢ ተቀራርቦ የተሰራ መንደር። 2.በተራራ ወይም በኮረብታ ላይ ያለና ለመኖሪያነት የሚሆን ሰፊ ሜዳ።

አምባላይ ስ ነጭ (ፈረስ)።

አምባሬይሌ ስ መልኩ ቀላ ያለ ዳለቻ ሆኖ ከጀርባው ወደ ሆዱ የሚወርዱ ነጫጭ ሽንትሮች ያሉበት፤ ረጅምና ከሁለት እስከ ሶስት ጊዜ የተጠማዘዙ ቀንዶች ያሉት፡ እሾሃማ ቁጥቋጦች ባሉባቸው ቆላማና ዝቅተኛ ስፍራዎች የሚኖርና አጋዘን የሚመስል የዱር እንስሳ።

አምባር ስ ከወርቅ ወይም ከብር፡ ... የሚሰራና ሴቶች በእጃቸው ላይ የሚያደርጉት ጌጥ።

አምባርሚያ ስ አምባር የሚደረግበት የእጅ ክፍል(ስእሉን እጅ ስር ተመ.)።

አምባሳደር ስ አገሩን ወክሎ እንዲሰራ በውጭ አገር የሚመደብ ባለስልጣን።

አምባሻ ስ ሽልማት ተደርጎበት በመፍራም ቂጣ መልክ የሚጋገር የስንዴ ዳቦ።

አምበባ ግ ስርያ የፈለገ ፍየል የእንስቲቱን ፍየል

የሂሳ ኣካል በእግሩና በኣገጩ እየገነተሰ ባባ የሚል ጩኸት ኣሰማ።

ኣምባዛ ስ መልኩ ጠቆር ያለ፣ ቀጫጭንና ረጃጅምም ፀጉር መሳይ ነገር አፉ ዳርና ዳር ያለው፣ ሥጋው ውስጥ ጥቃቅን እሾህ መሰል አጥንቶች የሌሉበት የአሳ አይነት፣ ጥቁሬ አሳም ይባላል።

ኣምባገነን ስ በህዝብ ሳይመረጥ በሃይል ስልጣን የያዘ፣ ሁሉን የሚያደርግና የመወሰን ሙሉ ስልጣን ለራሱ የሰጠና የህዝቡን ፍላጎት አፍኖ የሚገዛ መሪ ወይም መንግስት።

ኣምባጓሮ ስ ጠብ፣ ጥል።

ኣምቦ ስ ጨውነት ያለው ውሃ ወይም አፈር።

ኣምቦልክ "**ኢንቬሎፕ**"ን ተመ.

ኣምታር "*መተረ*¹" ስር "**መተሮ**"ን ተመ.

ኣምቻ "**ኣማች**" ስር ተመ.

ኣምና ስ አሁን ካለው አመት በፊት ያለው አመት፣ ያለፈው አመት።

ኣምፄ ስ ክረምቱ ካለፈ በኋላ በመስከረም የሚበራ ሰንጼ።

ኣምዛ ስ ተነባብሮ የተጋገረ እንጀራ፣ አነባበሮ።

ኣምድ ስ 1.ምሰሶ። 2.በአርእስትና በሀዳግ መካከል ያለ ወይም በተፃፈበት መካከል ለገፅ መክፈያ የሚተው ባዶ ቦታ። 3.በመፅሄት ወይም በጋዜጣ ላይ ሁልጊዜ አንድን ጉዳይ በተመለከተ የሚፃፍበት የመፅሄቱ አንድ ክፍል። *የሀዘን ኣምድ።*

ኣምደ ወርቅ ስ በቅኔ ማህሌት ውስጥ በስተቅድስት በኩል በሁለት በሮች መካከል የቆመ ኣምድ።

ኣእማድ ስ 1.የኣምድ ብዙ ቁጥር። 2.እንደ ተደራጊ፣ ተደራራጊ፣ አድራጊ፣ አደራራጊ፣ አስደራጊ፣ … ያሉ የግስ እርባታ ቅርፆች (ሰርአተ እርባታ)።

ኣእማደ ምስጢር ስ ምስጢረ ስላሴን፣ ሚስጢረ ስጋዌን፣ … የያዘ መፅሃፍ።

ኣምጃ ስ በደጋና በወይና ደጋ አካባቢ ጥቅጥቅ ብሎ የሚበቅል የቁጥቋጦ አይነት።

ኣምፋሮ "**እንፋሮ**"ን ተመ.

ኣምፖል(ኣምፑል) ስ በኤሌክትሪክ ሃይል አማካይነት ብርሃን ለመስጠት የሚችሉ ቀጫጭን ሽቦዎች በውስጡ የሚገኙበት፣ የተለያየ ቅርፅና መጠን ያለው የኤሌክትሪክ መብራት ብርጭቆ።

ኣምፖል ማቀፊያ ስ ከኤሌክትሪክ ሽቦ ጋር የሚያያዝና ኣምፖል የሚሰካበት ቀዳዳ ያለው የኤሌክትሪክ እቃ።

ኣሞሌ [ጨው] ስ ከባህር ውስጥ ሳይሆን መሬት ውስጥ በድንጋይ መልክ የሚገኝ ጨው (በድሮ ጊዜ ለመገበያያ እንደገንዘብ ሆኖ ያገለግል ነበር)።

ኣሞራ ስ 1.እንደጥንብ አንሳ፣ የሎስ፣ ጋጋኖ፣ … ያሉ ትላልቅ አእዋፍ። 2.(ዘይ.) ፈጣን፣ ቀልጣፋ። *ልጁ ኣሞራ ነው።* (ስእሉን በሚቀጥለው ገፅ ተመ.)

የኣሞራ ምሳ ስ ሲበስል ቀይ የሚሆንና ጣፋጭ ፍሬ ያለው የሃረግ አይነት፣ ፍሬውም የኣሞራ ምሳ ይባላል።

ኣሞርቲዛተር ስ በመኪናዎች ጎማ አጠገብ የሚገጠምና መኪናው በመጥፎ መንገድ ላይ እንዳይንገጫገጭ የሚረዳ አረጋጊ መሳሪያ።

ኣሞት "**ሃሞት**"ን ተመ.

ኣሞጪ ስ በና ነጭ ሽንኩርት የሚመስል ፍሬ የሚያፈራና የማይበላ የእፅዋት አይነት።

ኣሞጪ የመሰለ በጣም ነጭ የሆነ።

ኣሚረ የ"**ቀሰሰ**"ን 2ኛ ፍቺ ተመ.

ኣሚዳ ቅ አፍንጫ ጎራዳ፣ ደፍጣጣ።

ኣረህ ስ በገደል መካከል ያለ ተዳፋት ቦታ።

ኣረሆ ስ ከቦታ ቦታ እየተዘዋወረች የምትዘፍን ሴት።

ኣረመ ግ 1.ከእህል ጋር የበቀለን አረም ነቀለ። 2.አስተካከለ፣ አቀና፣ እርማት ሰጠ። 3.ስህተት ወይም ልክ መሆኑን እያረጋገጠ ተገቢውን ነጥብ ሰጠ (ለፈተና)። 4.ቀጣ፣ ገራ (ለባጌን)።

ማረሚያ ስ ማስተካከያ፣ ማሻሻያ (ለፅሁፍ)።

ማረሚያ ቤት ስ ወንጀል የሰራ ወይም ህግ ተላልፎ የተፈረደበት ሰው እስከ ቅጣቱ ፍፃሜ ድረስ የሚቆይበት ቦታ፣ እስር ቤት።

ኣረም ስ ከእህል ጋር አብሮ የሚበቅልና አስፈላጊ ባለመሆኑ ተነቅሎ የሚጣል ማንኛውም አይነት እፅዋት።

ኣረም ሜነበት ተወው፣ ችላ ኣለው (ለስራ፣ ለጉዳይ፣ …)።

ኣረሙቻ ስ አረም።

እርማት (እርምት) ስ 1.የሚታረም ወይም የሚስተካከል ስራ። 2. ማሻሻያ። *እርማት ተደረገበት።*

ታረመ ግ 1.ከአረም ፀዳ፣ አረሙ ተነቀለለት። *ጤፉ ታረመ።* 2.ተስተካከለ፣ ተሻሻለ (ፅሁፍ)። 3.ተሻሻለ፣ ጥሩ ሆነ (ጠባዩ)።

ኣረመመ ግ ዝም አለ፣ ከመናገር ተቆጠበ።

ኣርምሞ ስ ዝምታ ወይም ፀጥታ።

በኣርምሞ በዝምታ፣ በፀጥታ፣ በተመስጦ። *በኣርምሞ ኣዳመጠ።*

ኣረመኔ ቅ 1.ጨካኝ፣ ርህራሄ የሌለው። ስ

1

2

3

4

5

6

7

8

9

10

11

12

13

14

15

16

1. ጆፌ አሞራ
2. ዳክዬ
3. ጆብሬል
4. የሲጣን ዶሮ
5. ጉጉት
6. ዝዪ
7. ጅግራ
8. ጥንብ አንሳ
9. ሳቢሳ
10. ቆልማማጊት
11. ሲላ
12. ንስር
13. ገዶ
14. ገርጊስ
15. የወንዝአሞራ
16. ጋጋኖ

2.ሃይማኖት የሌለው፡ በጣኦት አምላኪ።

አረመደ ግ በእንጀራ፡ በዳቦ፡... ብትን በርበሬን ደመደመ ወይም አጠቀሰ።

ማርመጃ ስ ድልህ፡ በርበሬ።

አረማሞ ስ በአዝመራ ጊዜ ተፈላጊውን መልካም ፍሬ እንዳያፈራ ጥቀርሻ መሰል በሆነ የእህል በሽታ ተጠቅቶ የሚገኝ የበቆሎ፡ የገብስ፡... ዛላ።

አረማዊ ቅ አረመኔ የሆነ፡ የአረመኔ ወገን።

አረም "**አረመ**" ስር ተመ.

አረረ ግ 1.ተቃጠለ፡ ተከነ (ከሚፈለገው በላይ እሳት የበዛበት ምግብ ነክ ነገር)። 2.ተናደደ፡ በገነ። 3.በጣም አዘነ፡ ልቡ በሃዘን ተነካ። 4.ቀጨጨ፡ ማደግ የሚገባውን ያህል ሳያድግ ቀረ።

— **አረረበት** — አጣ፡ ተቸገረ። *ቆሎ አረረበት= ቆሎ እንኳን አጣ*።

አረረም መረረም ተወደደም ተጠላም።

አሩሩ ቅ ያረረ፡ የተቃጠለ።

እርር ምርር አለ ግ 1.በጣም አለቀሰ፡ ተንሰቀሰቀ። 2.በጣም አማረረ፡ ተማረረ፡ ተንገፈገፈ።

እርር ብሎ አለቀሰ ምርር ብሎ አለቀሰ።

እርር ኩምትር አለ ግ በጣም አረረ፡ ተናደደ።

አሳረረ ግ መታ፡ ሸነቆጠ፡ ገረፈ (በጅራፍ፡ በአርጩሜ)።

አረር ስ የጥይት እርሳስ።

አረሰ^{1} ግ በማረሻ ገመሰ፡ ተለመ፡ ሰነጠቀ (የእርሻ መሬትን)።

አርሶ በላ ስ አርሶ አደር፡ ገበሬ።

አርሶ አደር ስ ገበሬ፡ በግብርና ስራ የሚተዳደር ሰው።

ማረሻ ስ በእርፍ ላይ ተሰክቶ መሬትን ለመተለሚያ፡ ለመሰንጠቂያ፡ ለማረሻ የሚያገለግል ከብረት የሚሰራ የእርሻ መሳሪያ (ስእሉን "**ሞፈር**" ስር ተመ.)።

አራሽ ስ ገበሬ፡ አርሶ አደር።

እራሽ ስ ማሳ፡ የእርሻ ይዞታ።

እርሻ ስ የአዝርእት መዝሪያና ማብቀያ፡ የታረሰ ወይም የሚታረስ መሬት።

የእርሻ መኪና ስ ለእርሻ ስራ የሚያገለግልና በሞተር የሚሰራ መኪና፡ ትራክተር።

የእርሻ መኪና

የእርሻ ውጤት ስ ከእርሻ የሚገኝ ምርት።

አሳረሰ ግ በተለያየ ውሉ (በኪራይ፡ በእርቦ፡...) በመስማማት ሌላ ሰው እንዲያርስለት አደረገ።

አሳራሽ ቅ ባለመሬት ሆኖ ሌሎችን በማሳረስ የሚጠቀም።

አረሰ^{2} ግ አራስን ተንከባከበ (በምግብና በሚያስፈልገው ነገር ሁሉ)።

አራስ ስ 1.ከወለደች ብዙ ቀን ያልሆናት ሴት። 2.ጨቅላ ወይም ከተወለደ ብዙ ጊዜ ያልሆነው ህፃን ልጅ።

አራስ ነብር ሆነ በጣም ተቆጣ፡ ተበሳጨ።

አራስ ልጅ ስ ጨቅላ ወይም ከተወለደ ብዙ ጊዜ ያልሆነው ህፃን ልጅ።

አራሽ ቅ አራስን የሚንከባከብ (ብዙ ጊዜ ሴት)።

ማረሻ ስ የወለደች ሴትን ለመንከባከብ የሚዘጋጅ ምግብ።

ታረሰች ግ (አራስ ሴት) በጥሩ ሁኔታ እንክብካቤ ተደረገላት።

አረቀ ግ 1.እርጥበት ያለውን የጎበጠ እንጨት በእሳት ለብልቦ አቃና፡ ቀጥ አደረገ፤ ወይም ቀጥ ያለውን እርጥብ እንጨት በእሳት ለብልቦ አጎበጠ፡ ለመጠ። 2.በምክር ፡ በተግሳፅ፡... እንዲያስተካክል አደረገ (ጠባዩን)። 3.ያጋደለውን የአህያ ወይም የአጋሰስ ጭነት አስተካከለ። 4.መታ። *በዱላ አረቀው*።

***አረቀ**

እርቅ ስ ቀድሞ የነበረን ጥል ወይም ቅሬታ በማስወገድ የሚደረግ ስምምነት፡ ፍቅር፡ ሰላም።

እርቅ ወረደ ቀድሞ ሲል የነበረው ጥል ወይም ቅሬታ ተወገደ፡ ሰላም ሆነ፡ ስምምነት ተፈጠረ።

እርቀ ሰላም ስ በመካከላቸው ጠብ ወይም ቅሬታ በነበረባቸው ወገኖች መካከል የሚደረግ እርቅ፡ ስምምነት።

ታረቀ ግ ከተጣላው ወይም ከተቀየመው ሰው ጋር ስምምነት፡ ሰላም ፈጠረ።

አስታረቀ ግ ቂመኞችን አስማማ፡ በመካከላቸው ሰላም እንዲፈጠር አደረገ።

አስታራቂ ቅ በተጣሉ ወገኖች መካከል በመግባት እርቅ ወይም ሰላም እንዲፈጠር የሚያደርግ።

አስታራቂ [ሽማግሌ] ዝ.ከ.

ያስታራቂ ስ ለአስታራቂ ሽማግሌዎች የሚደረግ ግብዣ።

አረቄ^{1} ስ የአልኮል መጠጥ አይነት።

አረቄ^2

አረቄ መርፌ ስ አጭርና ቀጭን መርፌ፡ ጥልቅ መርፌ።

አረቄ^3

አረቄ ወገብ ቅ ወገበ ቀጭን።

አረበደ ግ በመቻኮልና በመሰፍሰፍ ወዲያ ወዲህ አለ፡ ተሯሯጠ።

አረቦን ስ ቀብድ፡ዋስትና ወይም መያዣ(ነገር)።

አረተረተ ግ በሰምሰማ ሮጠ።

አረንቋ ስ ረግረግ፡ ማጥ።

አረንዛ ስ 1.ብዙ ድንጋይ ያለበት ቦታ። 2.ጥቁር ድንጋይ የበዛበትና ውስጡ ውሃ የሚሰማው፡ ረግረግነት ያለው መሬት ወይም ቦታ።

አረንጓዴ ቅ 1.ለምለም ቅጠልን ወይም ሳርን የመሰለ የቀለም አይነት። 2.አልጌ።

***አረዘ**

እርዛት ስ የልብስ እጦት ወይም ችግር።

ታረዘ ግ የሚለብሰው አጣ።

አረደ ግ 1.የሰውን ወይም የእንስሳትን አንገት ስለት ባለው መሳሪያ ቆረጠ። 2.ቆረጠ። *እጆን በዚቃዋ አረደው*፡ 3.በበይ ቅርፅ አይነት መሬትን ገመሰ፡ አነደነደ፡ ነደለ። *መሬቱን አረደው*፡ 4.(ዘይ.) አታሰለ፡ ጉድ ሰራ።

አርዳኝ ሄደ አታሎኝ፡ ጉድ ሰርቶኝ ሄደ።

አረድ ቅ አታላይ፡ ሌባ።

አራጅ ስ በሬን፡ ላምን፡ ፍየልን፡ በግን፡ ... የሚያርድ፡ የመግፈፍና ብልት የማውጣት ችሎታ ያለውና ለሚሰጠውም አገልግሎት ገንዘብ ባለሙያ።

እርድ ስ 1.ለድግስ፡ ለግብር፡... የታረደ እንስሳ (በሬ፡ ላም፡ በግ፡ ...)። 2.ምሽግ፡ ጉድባ፡ ጉድጓድ።

ለእርድ ቀረበ ለመታረድ ቀረበ።

ያለእርድ ዋለ በበአል ቀን በግ፡ ዶሮ፡... እቤቱ ሳያርድ ቀረ።

ተራረደ ግ ተገዳደለ፡ ተጨፋጨፈ።

አረጻ^1 ስ የአንድ አካባቢ ነዋሪ ህዝብ።

አረጻ^2 "**ረጻ**" ስር ተመ.

አረጻ^3 ስ ፍግ ወይም ጥራጊ የሚፈስበት ቦታ።

አረጻ [መሬት] ስ የጻበረ መሬት።

አረጀ ግ 1.ሸመገለ። 2.አሮጌ ሆነ (ልብስ፡ እቃ፡ ...)።

እርጅና ስ ሽማግሌ ወይም አሮጌት መሆን።

አስረጀ ግ አሮጌት ወይም ሽማግሌ አደረገ።

አረገ ግ ከመሬት ወደ ሰማይ ወጣ። *ክርስቶስ ከመቃብር ተነስቶ ወደ ሰማይ አረገ*።

እርገት ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ክርስቶስ ወደ ሰማይ ያረገበትን ቀን ለማስታወስ በየአመቱ በግንቦት ወይም በሰኔ ወር ከፋሲካ በኋላ በአርባኛው ቀን ሃሙስ እለት የሚከበር በአል።

አሳረገ ግ የማሳረጊያ ወይም የመደምደሚያ ፀሎት አደረገ።

ማሳረጊያ ስ መጨረሻ፡ መደምደሚያ፡ መፈፀሚያ።

አረጋዊ (ብቁ.**አረጋውያን**) ቅ ሽማግሌ፡ አዛውንት።

አረግ ሬሳ "**ሃረግ**" ስር "**ሃረግ ሬሳ**"ን ተመ.

አረጠረጠ ግ 1.ቦረቀ፡ ፈነጠዘ። 2.አዘጠዘጠ፡ ወዲያ ወዲህ አለ።

አረጥራጭ ቅ አዘጥዛጭ።

አረጠች ግ እድሜዋ በመግፋቱ ምክንያት የወር አበባዋ ቆመ፡ መፀነስ፡ መውለድ አቆመች።

አረጥራጭ "**አረጠረጠ**" ስር ተመ.

አረጭ ስ ጭራ።

አረፈ ግ 1.እፎይ አለ፡ ድካሙን አስወገደ፡ እረፍት አደረገ። 2.ሞተ። 3.ከመናገር፡ አንድን ነገር ከመስራት፡... ተቆጠበ። 4.ወረደ፡(ቦታ ያዘ ተቀመጠ፡ በረረ(ከአየር ወደ መሬት፡ዛፍ፡...) *ንቡ ላዋሩ ላይ አረፈ / አውሮፕላኑ አረፈ*። 5.ተነካገለ፡ ተላቀቀ። *ከጭቅጭቅ አረፈ*። 6.በእንግድነት ተቀመጠ፡ ሰፈረ። *ከአገሩ ሲመጣ ወንድሙ ዘንድ አረፈ*።

ማረፊያ ስ 1.የእንግዳ መቆያ፡ መቀመጫ። 2.ቤት፡ መኖሪያ፡ መጠለያ። *ማረፊያ ሳይኖረው ትዳር ማሰብ የለበትም*።

ማረፊያ ቤት ስ እስር ቤት።

አረፍተ ነገር ስ አንድ የተሟላ ሃሳብን የሚይዝ የቃላት ስብስብ።

አረፍት ስ 1.መቀመጫ፡ ማረፊያ። 2.በገጠር ቤቶች ለእቃ ማስቀመጫነት እንዲያገለግል ከግድግዳ ጋር ተያይዞ የሚሰራ መደርደሪያ፡ ዘለንጋ።

እረፍ 1. እረፍ፡ ተው አታድርግ፡...። 2. እረፍት አድርግ።

እረፍት (እርፈት) ስ ማረፍ፡ እፎይ ማለት። 2.ለተወሰነ ጊዜ ከስራ፡ ከትምህርት፡ ከስብሰባ፡... ተለይቶ የሚቆይበት ጊዜ፡ ማረፊያ ጊዜ። 3.ሞት።

እረፍተ ቢስ (እርፈተ ቢስ) ቅ አርፎ ወይም ተቆጥቦ የማይቀመጥ፡ ቀዥቃዣ።

እረፍት የለሽ ቅ 1. ማረፊያ ጊዜ የሌለው

ሠተለ። 2. እረፍተ ቢስ።

አሳረፈ ግ 1.እረፍት፡ ፋታ እንዲያገኝ አደረገ። 2.ሸክምን አስቀመጠ። 3.ገላገለ፡ አዳነ። 4.ገደለ፡ አሳለፈ። *በዱላ ማጅራቱን ብሎ አሳረፈው*። 5.መሬት አስያዘ፡ አሳረደ (አውሮፕላን ላይ)።

አሳሬፈ (አሬፈ) ቅ እንደ እግር ኳስ፡ መረብ ኳስ፡ ቅርጫት ኳስ፡ ... ባሉ ስፖርታዊ ጨዋታዎች ላይ አንድ ተጫዋች በደንብ መጫወት ባይችል ወይም ቢደክመው በምትኩ ገብቶ ሊጫወት የሚችል ተጫዋች።

አሳርፈው ተው በለው፡ከልክለው።

አረፈረፈ ግ ረጨ፡ አርከፈከፈ።

አረፋ^{1} ስ እንደ ደ፡ ሳሙና፡ ሊም፡ ... በውሃ ሲበጠበጥ የሚፈጥረው ነጭ የሚኩረፈረፍ ነገር፡ ወይም የባሕር ውሃ በማእበል ሲገፋ የሚፈጥረውና ውሃው ላይ ተንሳፎ የሚታየው ነጭ ነገር።

አረፋ ደፈቀ በህመም፡ በድካም፡... የተነሳ ከአፉ አረፋ የሚመስል ነገር ወጣ።

አረፋ^{2} ስ አ.ድአል አድሃ።

አሬማጥ "ረመጠ" ስር ተመ.

አሬባራ ስ መጠኑ ርግብ የሚያክል፡ የጅራቱ ቀለም ነጭና ጥቁር፡ ሌላው አካሉ ጥቁርና አመድማ የሆነ የወፍ አይነት (ስእሉን ወፍ ስር ተመ.)።

አሬቲ ስ አመድማ መልክና ጥሩ ሽታ ያለው የተክል አይነት፣ ናትራን።

አራ ግ (ነውር) 1.አይነምድር ከሰውነቱ አስወጣ፡ ተፀዳዳ። 2.(ዘይ.) ተጨማለቀ፡ ተሞላቀቀ፡ ተንጠባረረ።

አር ስ 1. (ነውር) በገራ ወይም አይነ ምድር። 2. ቆሻሻ ፡ አሰር (የቅቤ)።

አሩን በላ 1.ክፉኛ ተደበደበ። 2.ተሰቃየ ወይም ለፋ።

አሩን ይጠፈጥፋል በጣም እርጅቷል።

አራም ቅ (ነውር፡ ስድብ) 1.ጨምላቃ፡ ባለጌ። 2.ፈሪ።

አራሙቻ "**አረም**" ስር ተመ.

አራማጅ "***ረመደ**" ስር ተመ.

አራም "**አራ**" ስር ተመ.

አራራ "**አረረ**" ስር ተመ.

አራራይ ስ ከሰባቱ ያሬዳዊ የዜማ አይነቶች አንዱ።

አራስ "**አረሰ**^{2}" ስር ተመ.

አራሽ "**አረሰ**^{1}" ስር ተመ.

አራሽ "**አረሰ**^{2}" ስር ተመ.

አራባ ስ የድር፡ የጥለት፡ ... ጥቅል፡ እበር፡ ቱባ።

አራባ "**ረባ**" ስር ተመ.

አራት ስ 1.በሶስትና በአምስት መካከል ያለ ቁጥር መጠሪያ፤ በአሃዝ ሲፃፍ '፬'፡ '4' ነው። ቅ 2.በሶስትና በአምስት መካከል ያለ ብዛትን የሚያሳይ። *አራት ጫማዎች*።

በአራቱም ማእዘን በሁሉም አቅጣጫ።

አራቱ መደብ ስ የመደመር፡ የመቀነስ፡ የማባዛትና የማካፈል ስሌት አጠቃላይ መጠሪያ።

አራት ማእዘን ስ 1.አራት ገፅ ወይም ጎን ያለው ማንኛውም ነገር። 2.የሰሜን፡ የደቡብ፡ የምስራቅና የምእራብ አቅጣጫዎች ጥቅል መጠሪያ። 3. መረብ።

አራት ነጥብ ስ በአረፍተ ነገር ማለቂያ ወይም መደምደሚያ ላይ የሚቀመጥ ስርአተ ነጥብ (።) ።

አራኛ ስ ጎረምሳነት።

አራዊት(ነጠ.ቁ. **አርዌ**) ስ 1.በዱር በገደል የሚኖሩ አውሬዎች በጥቅል የሚጠሩበት ስም። ቅ 2.(ዘይ.) ጨካኝ፡ አረመኔ፡ ክፉ።

አራዠ ግ አመመ፡ አሰቃየ፡ እረፍት ነሳ፡ አናወዘ፡ አስጨነቀ (ህመም፡ መድሃኒት፡ ...)።

አራዳ ስ 1. በከተማ ውስጥ የሚገኝ የገበያ ቦታ። 2.ዛሬ ፒያሳ እየተባለ የሚጠራው የአዲስ አበባ መሃል ከተማ የድሮ መጠሪያ። 3.(ዘይ.) ሙሉ፡ ብልጥ፡ ቀልጣፋ።

የአራዳ ልጅ/ሰው ንቁ፡ ብልጥ፡ ቀልጣፋ።

አራጅ^{1} ስ ረጅም ጅራት ያለውና ከአፉ ምጥምጥ ያለ፡ ቀፎ ደፍቶ ማር የሚበላ አውሬ፤ ፋደት።

አራጅ^{2} "**አረደ**" ስር ተመ.

አራጣ ስ ከፍተኛ የገንዘብ ብድር ወለድ።

አራጣ አበዳሪ ስ በከፍተኛ የወለድ መጠን ገንዘብ የሚያበድር ሰው።

አሬራ ስ የረጋ ወተት ተንጦ ቅቤው ከወጣ በኋላ የሚቀረው ቀጭን ወተት።

አርመን ስ የጉድጓድ ወይም የግንብ ወይም የካብ የጎን ስፋት።

አርማ ስ የአንድ ድርጅት፡ ማህበር፡ ... ህጋዊ መለያ ወይም ምልክት።

አርምሞ "**እረመመ**" ስር ተመ.

አርበኛ ስ ለአገሩ፣ ለወገኑ ክብርና ነፃነት ሲል በአገር ወዳድነት ከውጭ ወራሪ ጋር የተዋጋ ጀግና።

አርቢትር (አልቢትር) ስ በአንድ ስፖርታዊ ውድድር ወቅት እንደ ውድድሩ አይነት ከሜዳ ውጭ ወይም በሜዳ ውስጥ በመሆን ስፖርታዊ

ሀሳችን የሚቆጣጠርና ውሳኔ የሚሰጥ ሰው፤ ዳኛ።

አርባ ስ 1.በሰላሳ ዘጠኝና በአርባ አንድ መካከል ያለ ቁጥር መጠሪያ፤ በአሃዝ ሲፃፍ '፵'፥ '40'። 2.አንድ ሰው ከሞተ በሗላ በአርባኛው ቀን የሚደረግ ተዝካር። ቅ 3.በሰላሳ ዘጠኝና በአርባ አንድ መካከል ያለ ብዛትን የሚያሳይ። *አርባ ሰዎች*።

አርብ^{1} ስ በሃሙስና በቅዳሜ መካከል ያለው ቀን ስም፤ ከእሁድ ጀምሮ ሲቆጠር የሳምንቱ ስድስተኛ ቀን።

የአርብ ውሃ ስ አርብ እለት የተቀዳ ውሃ (ለሰንበት አክባሪዎች ተቀድቶ የሚቀመጥ)።

አርብ^{2} ስ 1.ድር የሚቋጠርበት የሸማኔ እቃ። 2.የማንኛውም ጨርቅ ጎን ወይም ወርድ ወይም ስፋት።

አርቲስት ስ 1. ሰአሊ። 2.እንደ ተዋናይ፥ ዘፋኝ ዳንኪረኛ ያለ የመድረክ ሰው።

አርቲቡርቲ ስ ፍሬከርስኪ ፡ የማይረባ ነገር።

አርቲፊሻል ቅ ተፈጥሮአዊ ያልሆነ፤ በሰው ሰራሽ። *አርቲፊሻል ጌጣጌጥ*።

አርታኢ (ብ.ቁ. **አርታኢያን**) ስ ብዙውን ጊዜ ሌላው ያቀረበውን ስራ (መፅሃፍ፤ መፅሄት፤...) ከህትመት በፊት የሚያስተካክልና የሚያቀናብር ሰራተኛ፤ ኤዲተር።

አርትእት ስ መፅሃፍን፣ መፅሄትን፣... በማረምና በማቀናት ለህትመት የማዘጋጀት ስራ።

አርነት ስ ነፃነት።

አርአያ ስ 1.ምሳሌ፤ አብነት። 2.ምስል፤ አምሳል፥ መልክ።

አርእስት ስ 1.የ "**ርእስ**"ን 1ኛና 2ኛ ፍቺ ተመ. 2. በስተመነሻ በኩል በግሶች ላይ በሚቀጠል ምእላድ("መ-") አማካይነት የሚመሰረት ቃል (ግሡ በ"አ" የሚጀምር ከሆነ "መ" ወደ "ማ-" ይለወጣል)። ለምሳሌ ብላ → መብላት/አበላ → ማብላት።

አርእስተ ነገር ስ የአንድ ነገር ወይም ሃሳብ መነሻ፤ ጭብጥ።

አርኬና ስ የንብ አውራ ወይም የምስጥ ንጉስና ንግስት ወይም የጣዝማ መኖሪያ።

አርያም ስ በክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ የእግዚአብሄር ዙፋን የተዘረጋበት ነው ተብሎ የሚታመን ከሰማያት በላይ ያለ የመጨረሻው ሰማይ።

አርዮስ ስ ክፉ፥ ጨካኝ፤ አረመኔ (ሰው)።

አርድእት ስ 1.የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታዮች የነበሩ አስራ ሁለቱ ሃዋርያትና ሰባ ሁለቱ ደቀመዛሙርት። 2.በሰባ ሁለቱ አርድእትና በሃዋርያት ስም የተፃፈ እንደአስማትና እንደ ልብወለድ ያለ መፅሃፍ።

አርጃኖ ስ አዞ የሚመስል፥ ቆዳው ሻካራና ጠንካራ የሆነ፥ በውሃ ውስጥና በድንጋይ ስር የሚኖር አውሬ።

አርጃኖ

አርጩሜ ስ ለበቅ ወይም ልምጭ።

አሮጌ ቅ 1.ሸማግሌ፥ ያረጀ። 2.የቆየ፥ ያረጀ፥ አዲስ ያልሆነ።

አሮጊት ስ ያረጀች ሴት፤ ባልቴት።

አሰላ^{1} ግ አደባ።

አሰላ^{2} "**ሰላ**^{2}" ስር ተመ.

አሰላ^{3} "**ሰላ**^{3}" ስር ተመ.

አሰላ^{4} "***ሰላ**" ስር ተመ.

አሰላሰለ ግ ስለ አንድ ነገር በተመስጦ ረዘም ላለ ጊዜ አሰበ፤ አወጣ አወረደ።

አሰረ ግ 1.እንዳይበተን፥ እንዳይዝረከረክ ወይም አንድ ላይ እንዲሆን በክር፥ በገመድ፥ በሲባጎ፥ ... በማያያዝ ቋጠረ። 2.ጥፋተኛ ወይም ወንጀለኛ ነው ተብሎ የተጠረጠረን ወይም ጥፋተኛ ወይም ወንጀለኛ የሆነን ሰው ያዘ፤ በህግ ቁጥጥር ስር አዋለ። 3.ወዲያ ወዲህ እንዳይንቀሳቀስ አደረገ፤ አንድ ቦታ አስቀመጠ። 4.አረፍተ ነገሩን በማሰሪያ አንቀፅ ደመደመ ወይም ጨረሰ።

እስር ስ 1.እስረኛ። 2.ብዛቱ ከአንድ በላይ የሆነና አንድ ላይ የታሰረ ወይም በተወሰነ መጠን ተደርጎ የታሰረ ነገር። *አንድ እስር ለንጨማ/አንድ እስር ቅዜ*። 3.(ሰዋ.ሰ.) ራሱን ችሎ የማይቆም ወይም የማይነገር (ምእላድ)።

እስር ምእላድ የ"**እስር**"ን 3ኛ ፍቺ ተመ.

እስር ቤት ስ በጥፋታቸው የተፈረደባቸው ወንጀለኞች ወይም ወንጀላቸው በመጣራት ላይ ያሉ ሰዎች በቁጥጥር ስር ሆነው የሚቀመጡበት ቦታ፤ ወህኒ ቤት።

እስረኛ ስ 1.በህግ ቁጥጥር ስር የዋለ ወይም በእስር ቤት ያለ ሰው። 2.በስራ ወይም በተለያየ ምክንያት ከቤት የማይወጣ ወይም ወደ ውጭ ወጥቶ የፈለገውን የማይሰራ ወይም የማይዝናና ሰው።

እስራት ስ በህግ ቁጥጥር ስር መዋል ወይም የሚዋል ድርጊት።

ተሳሰረ ግ 1.ተያያዘ፥ ተቆላለፈ፥ ተተበተበ።

2.ተንተባተበ፣ ተኮሳተረ። *አንደበቱ ተሳሰረ።* 3.በቅልጥፍና ወይም በድንገት መንቀሳቀስ አቃተው። *ሰውነቱ ተሳሰረ።*

አሰር¹ ስ 1.በመቀጫ ወይም በመፍቻ አማካይነት እንደ ገብስ፣ አጃ፣ ጤፍ ... ካሉ የእህል ፍሬዎች ላይ እየተገለፈፈ የሚወጣ የፍሬዎቹ ሽፋን፣ ገለባ፣ ጉሹ። 2.እፍታው የተነሳለት ውሃ።

አሰር ውሃ ስ የ"ቅራሪ"ን 2ኛ ፍቺ ተመ.

አሰር² ስ ኮቴ፣ ዱካ፣ ፈለግ።

አሰሰ ግ 1.የሚፈልገውን ለማግኘት እየተዘዋወረ መረመረ፣ ፈተሸ፣ ፈለገ። 2.በሁሉም አዳረሰ። *ከተማውን አሰሰና ተመለሰ።* 3.ምግብን በማበሻ ወሰወሰ፣ አሰሰሰ።

ማሰሻ ስ 1.ለምግብ ማሰሰሻ ወይም መወልወያ የሚያገለግል የተወቀጠ ጎመን ዘር ወይም ጎሎ ወይም የጥጥ ፍሬ። 2.ለምግብ መወልወያ የሚያገለግል እራፊ ጨርቅ።

አሰሳ ስ የሚፈልጉትን ነገር ለማግኘት ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ መመርመር፣ መፈተሽ፣ መፈለግ።

አሳሽ ቅ 1.የተደበቀ ነገርን እየዞረ የሚመረምር ወይም የሚፈትሽ። *አሳሽ ቡድን።* 2.ዘዋሪ።

አሰበ ግ 1.በአእምሮው ውስጥ ስለአንድ ነገር አወጣ አወረደ፣ አሰላሰለ። 2.አሰላ፣ ሂሳብ አደረገ። 3.ተጨነቀ፣ ሰጋ። 4.አስታወሰ፣ ትዝ አለው። *ያለፈውን ሳስበው ይገርመኛል።* 5.አቀደ፣ ቀየሰ፣ ነደፈ። *ነገ ናዝሬት ለመሄድ አስቢያለሁ።* 6.ፈለገ፣ ፈቀደ። *ለትዳር አስቢያታለሁ።* 7.በአንድ ጉዳይ ላይ ያገባኛል፣ ይመለከተኛል በማለት ተጨነቀ፣ ሃላፊነት ተሰማው። *ለአገሩ ያስባል፣ ለቤተሰቡ ያስባል።*

አሳቡን ጣለ ማሰብ፣ መጨነቅ ተወ።

አሳቢ ቅ ሃላፊነት የሚሰማው፣ የሚጨነቅ፣ የሚቆረቆር።

አሳብ "ሃሳብ"ን ተመ.

እሳቤ ስ ፅንሰ ሃሳብ።

ታሰበ ግ 1.ትዝ አለ፣ ታወሰ። 2.ታጨ፣ ተመለመለ። *ለከፍተኛ ስልጣን ታስቧል።*

ታስቦ ዋለ አንድ ልዩ ነገር የተፈፀመበትና መታወስ ያለበት እለት፣ ሌሎች በአላት በሚከበሩበት መልክ ሳይሆን በማስታወስ ብቻ ተከበረ።

መታሰቢያ ስ አንድን የተፈፀመ ድርጊት ወይም የሞተ ሰውን ለማስታወስ የሚደረግ ወይም የሚሰጥ ወይም የሚቆም ... ማንኛውም ነገር (ድግስ፣ ሃውልት፣ ህንፃ፣ ወይም ልዩ ልዩ እቃዎች)።

ታሳቢ ስ 1.ወደፊት ባንድነት ተጠቃሎ የሚታሰብ፣ ወደፊት የሚደመር ወይም የሚቀነስ የተወሰነ የገንዘብ መጠን። 2.አባል እንዲሆን የታሰበ፣ የታጨ።

ተሳሰበ ግ 1.ተሳሳ፣ ተቆረቆረ። 2.ተረዳዳ፣ ተደጋገፈ። 3.ተፈላለገ፣ ተፈቃቀደ (ለፍቅር፣ ለጓደኝነት፣ ለጋብቻ)።

አሳሰበ ግ 1.አስታወቀ፣ አስገነዘበ። 2.አስጨነቀ፣ አሰጋ። 3.አሰላ፣ ሂሳብ አስደረገ። 4.ትዝ እንዲል፣ እንዲታወስ አደረገ።

ማሳሰቢያ ስ ማስገንዘቢያ።

አሳሳቢ ቅ 1.አስጊ፣ አስፈሪ። 2.አስጨናቂ።

አስተሳሰበ ግ 1.አንዱ ለሌላው እንዲያስብ፣ እንዲጨነቅ አደረገ። 2.አገዘ፣ አብሮ አሰላ (ሂሳቡን)።

አስተሳሰብ ስ አመለካከት።

አሰንዳቦ ስ በእርጥብ ወይም በቆላ መሬት ላይ የሚበቅልና ከብቶች የሚበሉት ፍሬ ያለው የሳር አይነት።

አሰኘ¹ ግ አስፈለገ፣ አማረ። *ቡና አሰኝቶኛል።*

አሰኘ² "*ሰኝ" ስር ተመ.

አሰድ [አሳት] ስ በሃምሌ ወር የሚወጣ የኮከብ አይነት፣ በተለምዶ "ኮከብ ቆጠራ"ን ተመ.

አሰገረ¹ ግ አጠመደ (አሳን)።

አሰገረ² ግ አንድ ቀን አሳለፈ፣ ዘለለ። *በዚህ ወር ሰኞ የዋለችው ልደታ በሚቀጥለው ወር ማክሰኞን አሰግራ ረቡእ ትውላለች።*

አሲድ ስ 1.ከተለያዩ ንጥረ ነገሮች የሚገኝ፣ ፈሳሽ የሆነ፣ የመርዝነት ባህሪ ያለውና ለልዩ ልዩ አገልግሎት የሚውል ኬሚካላዊ ንጥረ ነገር። 2.እንደ ሎሚ፣ ብርቱካን፣ ኮምጣጤ ... ባሉ ፍራፍሬዎች ውስጥ የሚገኝና የሚኮመጥጥ ጣእም ያለው ንጥረ ነገር።

አሲዳም ቅ 1.(ስድብ) ሲበላ የማይጠረቃ፣ ሆዳም። 2.ልብስ፣ ጫማ፣ ገንዘብ፣ ... ቶሎ የሚያልቅበት ወይም የማይበረክትለት።

አሳ ስ በስንጥቡ እየተነፈሰ በውሃ ውስጥ የሚኖርና ከውሃ ውጭ ሊኖር የማይችል፣ ለምግብነት የሚያገለግል ውሃ ውስጥ ከሚኖሩ ፍጥረታት አንዱ።



አሳ

ኣሳ ለቃሚ ስ የወንዝ ኣሞራ፤ ምንቃረ ረዥም የሆነችና ኣሳ እየበላች የምትኖር ኣሞራ።

ኣሳ ነባሪ (ኣሳ አንበሪ) ስ በውቅያኖስ ውስጥ የሚኖርና ከኣጥቢ እንስሳት ጋር የሚመደብ በጣም ትልቅ የኣሳ ኣይነት።

ኣሳ ነባሪ

ኣሳ ኣውጪ ስ ኣሳ ለቃሚ።

ኣሳ ኣድን ስ ነጭና ጥቁር መልክ፤ ኣጭርና ሹል ምንቃር፤ እንዲሁም ኣጭር ቅልጥም ያለው፤ ብዙውን ጊዜ በሃይቆች ኣካባቢ የሚገኝና ኣሳ በመመገብ የሚኖር፤ በመጠን ዋኔን የሚያክል የወፍ ኣይነት።

ኣሳ ኣጥማጅ ስ ኣሳን ኣጥምዶ በመሸጥ የሚተዳደር ሰው፤ ኣሳ ኣስጋሪ።

ኣሳ ወርቂት ስ መካከለኛ መጠንና ወርቃማ መልክ ያለው የኣሳ ኣይነት።

[የ]ኣሳ ዘይት ስ በባህር ውስጥ ከሚገኝና ትልቅ ከሆነ አንድ ኣይነት የኣሳ ጉበት የሚዘጋጅ፤ ቫይታሚን "ዲ"ና "ኤ" ያለው፤ ለመድሃኒትነት የሚያገለግል የዘይት ኣይነት።

ኣሳማ ስ 1.ሸካራው ድፍን፤ እግሮቹ ኣጫጭሮች፤ ኣፉ ሞጥሞጥ ያለ፤ ያገኘውን ነገር የሚመገብ፤ ከኣጥቢ እንስሳት ወገን የሚመደብ እንስሳ። 2.(ስድብ፤ ዘይቤ) ሆዳም፤ በቃኝ የማይል።

ኣሳማ

ኣሳማ "**ስማ**" ስር ተመ.

ኣሳማ "**ኣማ**" ስር ተመ.

ኣሳር ስ መከራ፤ ጭንቅ፤ ስቃይ።

ኣሳሩን በላ ተሰቃየ፤ ተቸገረ፤ መከራውን ኣየ።

ኣሳረኛ ቅ መከረኛ፤ ጎስቋላ።

ኣሳሽ "**ኣሰሰ**" ስር ተመ.

ኣሳቢ "**ኣሰበ**" ስር ተመ.

ኣሳብ "**ሃሳብ**"ን ተመ.

ኣሳቻ "**ሳተ**" ስር ተመ.

ኣሳጣ "**ኣጣ**" ስር ተመ.

ኣሳጣ ግ 1.አጋለጠ፤ ኣጋፈጠ። 2.ስም ኣጠፋ፤ ኣሰማ።

ኣሳጭ ቅ ኣጋፋጭ።

ኣስ—(በቁ.) ከግስ በፊት እየገባ ኣስደራጊነትን ወይም ኣድራጊነትን የሚገልፅ እስር ምእላድ። *መጣ → ኣስመጣ/ተኛ → ኣስተኛ።*

ኣስማት ስ ለበጎ ወይም ለመጥፎ ነገር ማስፈፀሚያ ይሆናል ተብሎ የሚደረግ ድግምት፤ ምትሃት።

ኣስማተኛ ስ ኣስማት ማድረግ የሚችል ሰው፤ ምትሃተኛ።

ኣስም ስ የመተንፈስ ችግር የሚያስከትል የበሽታ ኣይነት።

ኣስር ስ 1.በዘጠኝና በኣስራ ኣንድ መካከል ያለ ቁጥር መጠሪያ፤ በኣሃዝ ሲፃፍ "10"፤ "፲" ነው። 2.ቅ በዘጠኝና በኣስራ ኣንድ መካከል ያለ ብዛትን የሚያሳይ። *ኣስር ተማሪዎች።*

ኣስር ኣለቃ ስ ከኣምሳ ኣለቅነት በፊት የሚሰጥ ወታደራዊ ማእረግ።

ኣስር ጊዜ (ኣስሬ) በተደጋጋሚ። *ኣንዴ ነግሬሃለሁ ኣስር ጊዜ ኣትጨቅጭቀኝ።*

ኣስርቱ ቃላት/ትእዛዛት ስ በመፅሃፍ ቅዱስ ውስጥ እንደተገለፀው ከእግዚአብሄር በሙሴ በኩል ለሰዎች የተሰጡ ኣስሩ ትእዛዛት።

ኣስራት ስ ከኣስር ኣንድ የሚከፈል ግብር።

ኣስራት በኩራት ስ በመፅሃፍ ቅዱስ ውስጥ በታዘዘው መሰረት ለእግዚአብሄር ወይም ለቤተ መቅደስ የሚሰጥ የእህል፤ የወይን፤ የዘይት ኣስራት፤ እንዲሁም የሰው ወይም የእንስሳ የመጀመሪያ ወይም የበኩር ልጅ።

ኣስቤስቶስ ስ ነጭ ወይም ግራጫ መልክ ያለውና ለስላሳ የሆነ የቃጫ ክር የሚመስል፤ በሰሌዳ ወይም በቆርቆሮ መልክ የሚሰራና እሳት ወይም ሙቀትን መቋቋም የሚችል፤ ከመሬት ውስጥ የሚገኝ ማእድን።

ኣስቤዛ ስ የወር የቤት ወጪ።

ኣስብ ስ ለአረኛ፤ ለቤት ሰራተኛ፤ ... የሚሰጥ የስራ ዋጋ፤ ምንዳ።

ኣስተምህሮ "***መሃረ**" ስር ተመ.

ኣስተነከረ ግ ኣሰረገጠ፤ ኣፅንኦት ሰጠ። *መልእክቱን ኣስተንክሮ ነገረኝ።*

ኣስተናበረ ግ 1.አንድን ስብሰባ ወይም ዝግጅት ኣቀናበረ፤ ኣዘጋጀ፤ መራ። 2.ኣሳለፈ፤ በበረከት እያስተናገደ ኣስተናገደ፤ ጋዜ በድግስ፤ በማብላት፤... ጊዜ።

አስተናባሪ ቅ 1.አንድን ስብሰባ ወይም ዝግጅት የሚያቀናብር፡ የሚመራ። 2.አስተናጋጅ፡ አሳላፊ (በድግስ፡ በግብዣ፡... ላይ)።

አስተናግር (እፀፋርስ) ስ ቅጠሉ ለስላሳና ለፋ ለፋ ያለ፡ ግንዱ ውስጡ ክፍት ሆኖ በእሾህማ ሽፋን ውስጥ የታቀፉ ጥቋቁርና ጠፍጣፋ ፍሬዎች ያሉት አነስተኛ የእፅዋት አይነት።

አስተኔ እንደ_ ያለ፡ _መሰል በማለት ብዙን ወይም አይነትን ለመግለፅ የሚያገለግል ቃል። *ቢጫ አስተኔ*።

አስተዋለ ግ 1. አተኩሮ ተመለከተ፡ በደንብ አየ። 2. ተገነዘበ፡ አሰበ።

አስተዋይ ቅ 1.ብልህ፡ አዋቂ፡ የሚያመዛዝን። 2.ተመልካች፡ ታዛቢ።

አስተያየት "**አየ**" ስር ተመ.

አስተጋባ ግ 1.አንድን የድምፅ አይነት ተቀብሎ እንደገና ጎላ አድርጎ ወይም ሞቅ ብሎ አሰማ። 2.የሌላውን ሰው ሃሳብ ወይም አስተያየት እንደሰሙየው ሆኖ ገለፀ ወይም አስታወቀ። 3.አንድን ሃሳብ ወይም አስተያየት ለሌሎች ገለፀ ወይም አስታወቀ።

አስታ (አስቴ) ስ 1.በደጋ አካባቢ ችፍግ ብሎ የሚበቅል፡ ትንሹ የጥድ ቅጠል የሚመስል የቁጥቋጦ አይነት (እንጨቱ ሲሰበቅ እሳት ይወጣዋል)። 2.እንጨትን በእንጨት በመሰበቅና በማፋተግ እሳት የማውጣት ድርጊት። 3.በአስቴ እሳት የተተኮሰ የክንድ ላይ ጠባሳ።

አስትሮኖሚ ስ ስለ ፀሃይ፡ ጨረቃ፡ ከዋክብትና ስለመሳሰሉት አካላት የሚያጠና የእውቀት ዘርፍ።

አስከሬን ስ ህይወት የሌለው ወይም በድን የሆነ የሰው አካል፡ ሬሳ።

አስከሬን መስሏል በጣም ከስቷል።

አስኳል ስ 1.በዶሮ፡ በወፍ፡... እንቁላል ውስጥ የሚገኝ ቢጫው ክፍል። 2. (በዶ.) ዋና ፍሬ ነገር።

አስፋልት ስ ከተፈጨ ድንጋይና ከሬንጅ ድብልቅ ለመንገድ እንዲሆን ተደምጦ የተሰራ መንገድ።

አሸ ግ 1.እህልን ወይም ፍሬን ከገለባ ወይም ከሽፋኑ ለመለየት በሁለት እጆች መዳፍ መሃል በማስገባት አፍተለተለ። 2.በደንብ እንዲገናኝ ወይም እንዲዋሃድ አድርጎ አበዛ (ሊጥን፡ ተልባን፡...)። 3.አለፋ፡ አለሰለሰ (ቆዳን)። 4.ወለምታን ለመመለስ፡ ውልቃትን ለመግጠም፡ ሙቀትን ለማግኘት ወይም እድፍን ለማውጣት ሰውነትን በእጅ አፍተለተለ። 5.ቆሻሻው እንዲለቅ በደንብ ፈገፈገ፡ አጠበ (ልብስን ሳሙናን...)። 6. በደንብ አድርጎ ደበደበ፡ ረገጠ። 7.ቀጠቀጠ፡ አኮላሸ (የበሬን፡ የበግን፡... አባለ ዘር)። 8.አለፋ፡ አደከመ፡ ደጅ አስጠና።

ታሸ ግ 1.ተለጠጠ፡ ተጀነነ። *በጠየቀው አምታሸ መለሰልኝ*። 2.ለገመ፡ ፈጠን ብሎ ለመስራት ፈቃደኛ ሳይሆን ቀረ።

ተሻሸ ግ 1.ሰውነት ለሰውነት ተነካካ፡ ተፋተገ። 2.ሰውነትን እርስ በእርስ ተደባበሰ (ተቃራኒ ፆታ)። 3.ከመታሸት፡ ከመፋተግ የተነሳ ተበላሸ፡ ተንሳቀለ (ወረቀት፡ ፋይል፡...)።

አሻሸ ግ ደባበሰ፡ ዳሰሰ። *ፀጉሩን አሻሸ*።

አሸለ ግ 1.ጨመረ፡ አከለ። 2.ለካ፡ ከነዳ።

አሻል ስ በሂሳብ የተደረገ ተጨማሪ ድር።

እሸል ቅ ተጨማሪ።

አሸመ ግ ወደውስጥ ጎነጎነ፡ ቆነነ፡ ሰራ (ፀጉርን)።

እሽም ስ በመፍረሙ የተጎነጎነ የፀጉር አሰራር አይነት።

አሸቦ (አሻቦ) ስ ጥሬ ጨው።

አሸቦ መሰለ ነጣጣ፡ አመዳም ሆነ።

አሸን ስ መሬት ውስጥ ተፈልፍሎ ከቆየ በኋላ ብዙውን ጊዜ በክረምት መግቢያ አካባቢ ከጉድጓዱ በብዛት እየወጣ የሚርመሰመስና ወደ ሰማይ የሚበር የምስጥ አይነት፡ ክረምት አግቢም ይባላል።

አሸን

አሸን ነው ከብዛቱ የተነሳ ቁጥሩን መገመት ያስቸግራል፡ እጅግ ብዙ ነው።

እንደ አሸን ፈላ በብዛት ወጣ፡ ታየ።

አሸንክታብ ስ በረዥም ማተብ ላይ ከወርቅ ወይም ከብር፡ ... የተሰሩ ትናንሽ ጌጦች የተሰኩበት በአንገትና በአንድ ትከሻ ብቻ የሚጠለቅና በሁለተኛው ትከሻ በኩል ከብብት ስር እስከ ዳሌ የሚደርስ የሴቶች ጌጥ።

አሸንዳ ስ 1.ከብረት ወይም ከቆርቆሮ፡... የሚሰራ፡ በቤት ክፈፍ ዙሪያ የሚውል፥ ውስጡ ክፍት የሆነ የውሃ መውረጃ፤ ጎረንዳዎ እየተባለም ይጠራል። 2.ፈሳሽ ነገር የሚያልፍበት እንደ ቱቦ ያለ ነገር።

አሸክት "**አሸክት**"ን ተመ.

አሸዋ ስ በወንዝ፡ በባህር ዳርቻና በበረሃማ አካባቢ የሚገኝ ደቃቅ የድንጋይ አይነት።

አሸዋ ግርፍ ስ በአሸዋ፡ በደቃቅ ጠጠርና በሲሚንቶ ድብልቅ የተለሰነ የቤት የውጭኛው

ግድግዳ።

አሸዋማ ቅ አሸዋ የበዛበት (ስፍራ)።

አሸገ ግ 1.እንዳይገለጥ ወይም እንዳይፈታ ጠቅልሎ በማሸጊያ አያያዘ፤ ሸፈነ (እቃን)። 2.በመጣበቅ ወይም በመቋጠር ዘጋ (ፖስታን)። 3.ከሚመለከተው ወይም ባለመብት ከሆነ አካል በስተቀር በሌላ አካል እንዳይከፈት በላዩ ላይ ማህተምና ፊርማ የተደረገበትን ጽሁፍ በመለጠፍ ዘጋ (ለምሳሌ ቤትን፤ ካዝናን፤ ...)። 4.(ምግብን፤ መጠጥን፤ መድሃኒትን፤ ...) በቆርቆሮ ወይም በላስቲክ፤ ... ውስጥ ጨምሮ መረገ፤ ዘጋ፤ ደፈነ።

እሽግ ቅ የተጠቀለለ ወይም የታሸገ ማንኛውም እቃ (ብዙውን ጊዜ ገና አገልግሎት ላይ ያልዋለ እቃ)።

የታሸገ ምግብ ስ በቆርቆሮ፤ በጠርሙስ፤ በላስቲክ፤... ውስጥ በመታሸግ የተዘጋጀና ለገበያ የሚቀርብ ምግብ።

አሹ አሰይ፤ እንኳን፤ ይሁን ለማለት የሚባል ቃል።

አሹራ ስ በንብረት ሽያጭ ጊዜ ለመንግስት የሚከፈል ግብር።

አሹቅ "ሾቀ" ስር ተመ.

አሻ¹ "ሻ²" ስር ተመ.

አሻ² አይ፤ አይሆንም፤ አይደለም።

አሻል¹ ስ 1.ቀይነትና ነጭነት ያለው ጠጉር ወይም አሸዋ። 2.በመረሬና በቀይ አፈር መካከል ያለ ለስላሳ መሬት፤ አሸልሴ። 3.በአራት እግሮቹ ጫፍ ላይ ነጭ ያለበት እንስሳ (በሬ፤ ፈረስ፤...)። ቅ 4.ግንባሩ ላይ ነጭ ያለበት (እንስሳ)።

አሻል² "**አሸለ**" ስር ተመ.

አሻመደ ግ በላ በብዛት።

አሻራ ስ የጣት የውስጠኛው ክፍል እንደ መስታወት ባለ አካል ላይ ሲያርፍ የሚተወው ዱካ ወይም ጣትን ቀለም አስነክቶ ማንኛውም ነገር ላይ ሲጫኑት የሚታየው ምልክት።

አሻራ

አሻራ ቢስ ቅ እድለ ቢስ፤ ገደ ቢስ።

አሻሮ ስ ለጠላ መጥመቂያ የሚሆንና በመጠኑ አረር እስኪል የተቆላ የገብስ ወይም የስንዴ ወይም የበቆሎ እህል።

አሻሮ ሆነ አረረ።

አሻቦ "**አሸበ**"ን ተመ.

አሻንጉሊት ስ በልዩ ልዩ ቅርፅና አምሳል (በሰው፤ በእንስሳ፤ ...) ከጨርቅ፤ ከፕላስቲክ፤... የሚሰራ የልጆች መጫወቻ።

አሻጥረኛ "**ሻጠረ**" ስር ተመ.

አሻግር ግ.ከ.

አሻፈረ

አሻፈረኝ አለ ግ እምቢ፤ አልታዘዝ፤ አልሰራ፤ አልፈልግም፤ ... አለ።

አሽሙር ስ አግቦ፤ ሽሙጥ፤ ምፀት።

አሽሙረኛ ቅ አግበኛ፤ አሽሟጣጭ።

አሽሟጣጭ¹ ስ በጎራዴ አፎት ጫፍ ላይ የሚገኝ ድቡልቡል ጌጥ።

አሽሟጣጭ² "**ሽሞጠጠ**" ስር ተመ.

አሽቆመቆመ "**ሽቆመቆመ**" ስር ተመ.

አሽከር ስ 1.ሎሌ፤ አገልጋይ። 2.እድሜው ከ7–ና አመት የሆነ ልጅ፤ ብላቴና (ጎንደር፤ ጎጃም)።

አሽኩቴ ስ እንደ በሶ ብላ ያለ፤ አበባው ቢጫ የሚመስልና ሽታው ጣፋጭ የሆነ የእፅዋት አይነት።

አሽክላ ስ 1.ለቀፎ ወይም ለወጥመድ መስሪያ የሚያገለግል፤ ፍሬውን ልጆች ለጌምሌጥ መስሪያ የሚጠቀሙበት የሃረግ አይነት። 2.መአዛው ጣፋጭ የሆነና ለጥርስ መፋቂያ የሚሆን የእፅዋት አይነት።

አሽክት (አሽክት) ስ መልኩ ጠቆር ያለና መጠኑ ድንብላል የሚያክል፤ ጠጣር ፍሬ ያለው እሾሃማ የሆነ ሃረግ መሰል አነስተኛ የእፅዋት አይነት። ፍሬውም አሽክት ይባላል።

አሽንበበ ግ 1.ነገር አጣመመ። 2.አሽቃበጠ። 3.ዳርዳሩን ዞረ፤ አስፈራራ።

አሽንባቢ ቅ 1.ነገረ ጠማማ። 2.አሽቃባጭ።

አሽንበጠ ግ አሽሟጠጠ።

አሽንባጭ ቅ አሽሟጣጭ።

አሾለቀ ግ አሾልኮ፤ አሾልቆ አየ።

አቀረቀረ ግ አንገቱን ጎንበስ አደረገ፤ መሬት መሬት አየ።

አቀበ ግ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ለመስዋእት የሚሆነውን ስንዴ በመልቀምና በመፍጨት ቤተክርስቲያንን አገለገለ።

አቃቢ ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ለመስዋእት የሚሆን ስንዴ በመልቀምና በመፍጨት እንዲሁም ለበአል የሚሆን ውሃ ቀድቶ በማቅረብ ቤተክርስቲያንን የሚያገለግል (ባሕታዊ፤ መነኩሴ)።

ኣቃቢት ስ የኣቃቢነት ስራ የምታከናውን መነኩሲት።

***ኣቀበ**

ታቀበ ግ ተቆጠበ (ከመናገር ወይም ከማድረግ)።

ተኣቅቦ ስ "ድምፅ" ስር "**ድምፀ ተኣቅቦ**"ን ተመ.

ኣቀበት (ኣቀብ) ስ ዳገት።

ኣቀነቀነ^{1} ግ ኣቀመቀመ፤ ኣበቀለ (ቢ.ያ)።

ኣቀነቀነ^{2} "**ቀነቀነ**^{2}"ን ተመ.

ኣቀንጭራ በፍጥነት የሚስፋፋና በእህል ሰብል ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርስ የአረም ኣይነት፤ ጸሃ ነቀል።

ኣቀደ ግ ወሰነ፤ ነደፈ፤ ቀየሰ።

ኣቅድ ስ 1.እቅድ። 2.ስልት፤ ዘዴ፤ ብልሃት። *የጠር ኣቅድ ያውቃል*። 3.መልክ፤ ስርኣት፤ ጥሩ ቅርፅ። *የቤቱ ኣሰራር ኣቅድ የለውም*።

ኣቅደ ቢስ ቅ ያልተስተካከለ፤ የማያምር።

እቅድ ስ በተወሰነ ጊዜ ሊሰራ የተወሰነ፤ የታሰበ፤ የተቀየሰ ስራ።

ኣቀጠለ ግ 1. ከተቆረጠ ወይም ከተመለመለ በሂላ እንደገና ቅጠል ኣወጣ፤ ኣቈጠቈጠ። 2.ጠገነ፤ ዳነ፤ እንደበፊቱ ሆነ (የተሰበረ አጥንት)።

ኣቀፈ ግ 1.በክንዱ ወደ ደረቱ ኣስጠግቶ ያዘ። 2.ከበበ፤ በዙሪያ ሆነ። *ሊሊ ጋደኛን ኣቅፎ የያዘው ብረት ዝጓል*። 3.ኣሰጠጋ፤ በስሩ ያዘ። *ህዝብ ሽፍቶቹን ኣቅፎ ይዟቸዋል/ መስሪያ ቤቱ በስሩ ሰባት ድርጅቶችን ያቅፋል*።

ማቀፊያ ስ 1.መታቀፊያ። 2.አንድን ነገር ዙሪያውን ኣቅፎ የሚይዝ። *ለምግብ ማቀፊያ /ወረቀት ማቀፊያ*።

ኣቃፊ ቅ የ"**ማቀፊያ**"ን 2ኛ ፍቺ ተመ.

እቅፍ ቅ 1. በአንድ ጊዜ በኣንድ ወይም በሁለት ክንድ መሃል ሊያዝ የሚችል መጠን። *ኣንድ ኣቅፍ ኣገዳ*። 2.አንድን ነገር ኣቅፎ ለመያዝ የሚያስችል የክንድና የደረት ኣካባቢ።

እቅፍ ኣበባ ስ ለስጦታ እንዲሆን በርከት ብሎና በአንድ ላይ ታስሮ የተዘጋጀ ኣበባ።

እቅፍ ዶሮ ስ 1.በሁለት ክንፎቿ ውስጥ ጫጩቶቿን የታቀፈች ዶሮ። 2.ጫጩቶችን ለመፈልፈል እንቁላል ታቅፋ የተቀመጠች ዶሮ።

እቅፎሽ ስ እቅፍ።

ታቀፈ ግ በክንዱ ወይም በእጁ ወደ ደረቱ ጠጋ አድርጎ ያዘ።

መታቀፊያ [ጨርቅ] ስ ህፃን ልጅን ጠቅልሉ ወይም ሸፍኖ ለመያዝ የሚያገለግል ጨርቅ፤ ፎጣ፤...።

ኣሳቀፈ (ኣስታቀፈ) ግ 1.ጫጩቶች እንድትፈለፍል ዶሮን እንቁላሎቿ ላይ እንድትቀመጥ ኣደረገ። 2.ደግፎ እንዲይዘው ዙሪያውን ኣደረገ (ኣፈርን፤ ድንጋይን በተክል ዙሪያ)።

ኣስታቅፎ ሄደ ለሌላ ሰው ትቶ ወይም ጥሎ ሄደ። *ልጆቹን ኣስታቅፋው ሄደች/ ሃብቱን ለሚስቱ ኣስታቅፏት ሄደ* ።

ኣቁሳ ስ የጅራፉን እጀታና ጅራፉን የምታያይዝ ቀጭን ገመድ(ስእሉን ጅራፍ ስር ተመ.)።

ኣቁማዳ ስ ሰልቻ።

ኣቁዳማ ስ በጥንት ጊዜ ጆብዱ የስራ ሰው ግንባሩ ላይ የሚያንጠለጥለው ጌጥ።

ኣቁጣር "ቆጠረ" ስር ተመ.

ኣቃሰተ "ቃሰተ" ስር ተመ.

ኣቃቂር ስ ቂንጥ።

ኣቃቂር ኣወጣ ቂንጥ ኣወጣ።

ኣቃቂር ኣውጪ ቅ ቂንጥ ኣውጪ።

ኣቃቂረኛ ቅ ኣቃቂር የሚያወጣ።

ኣቃቅማ ስ በቆላማ አካባቢ መሬት ላይ ተሰጥፎ የሚበቅል የእሾህ ኣይነት፤ ኩርንችት።

ኣቃቢ " ኣቀበ" ስር ተመ.

ኣቃቢት ዘ.ከ.

ኣቃቤ ህግ ስ ህጎች መከበራቸውንና በትክክል በስራ ላይ መዋላቸውን የሚቆጣጠር፤ ህገወጥ ድርጊቶች እንዳይፈፀሙ የሚከላከልና ከተፈፀሙም ተከታትሉ ለፍርድ የሚያቀርብ የመንግስት ሹም ወይም ኣካል።

ኣቃቤ ሰራይ ስ የባህል መድሃኒት ኣዋቂ።

ኣቃተ ግ 1.ተሳነ። 2.ኣስቸገረ፤ ኣልበገር ኣለ፤ ኣሸነፈ።

ኣቃፊ "ኣቀፈ" ስር ተመ.

ኣቅል ስ ኣደብ፤ ትእግስት።

ኣቅለ ቢስ ቅ ጠልቧላ፤ ከውካዋ፤ ትእግስት ወይም ኣደብ የሌለው።

ኣቅማማ ግ ኣንድን ነገር ሳድርግ ኣላድርግ ብሎ ኣሰበ፤ አወላወለ፤ ኣመነታ።

ኣቅም ስ ችሎታ፤ ጉልበት፤ ሃይል፤ ብርታት። *ይህንን ለማከረፍት ኣልቻልም ከኣቅሜ በላይ ነው /ግንዱው ከባድ ነው ለመሸከም ኣቅም የለኝም*።

ለኣቅመ ሄዋን ደረሰች በእድሜና በኣካል ከልጅነት ወደ ኮረዳነት ከፍ ኣለች፤ ወደ እናትነት ደረጃ ደረሰች፤ ቆነጀች።

ለኣቅመ አዳም ደረሰ በእድሜና በኣካል ከልጅነት ወደ ጉርምስና ደረጃ ከፍ አለ፤ ወደ

አባትነት ደረጃ ደረሰ።

አቅሙን አያውቅ ከችሎታው፣ ከጉልበቱ፣... በላይ ለማድረግ የሚሞክር ወይም የሚመኝ።

ከአቅም በላይ ሆነ አስቸጋሪ፣ ከባድ ሆነ።

አቅመ ቢስ ቅ ጉልበት የሌለው፣ ደካማ።

አቅራቢያ "ቀረበ" ስር ተመ.

አቅራብ [ውሃ] ስ በጥቅምት ወር የሚወጣ የኮከብ አይነት። በተጨማሪ **"ኮከብ ቆጠራ"**ን ተመ.

አቅርቦት "ቀረበ" ስር ተመ.

አቅድ "አቀደ" ስር ተመ.

አቅጣጫ ስ 1.አንፃር፣ መስመር፣ በኩል። *ፀሃይ ሁልጊዜ በስተምስራቅ አቅጣጫ ትወጣለች።* 2.አዝማሚያ፣ ሁኔታ። *የነገሩ አቅጣጫ አላማረኝም።*

አቆረ ግ (ጎድጓዳ ቦታ) ውሃ ቋጠረ፣ ያዘ፣ አጠራቀመ። 2.በስራ ወይም በህመም ምክንያት ሰውነት ደም ወይም መግል ያዘ።

አቆር አለ ግ በመጠኑ አበጠ፣ እንቅራት አወጣ።

አቆስጣ ስ በብዛት ጠቆር ያለ መልክ ያለው፣ ከቁመቱ ጋር ሲወዳደር ርዝመቱ ትልቅ የሆነ፣ በውሃ ውስጥና ከውሃ ውጪ መኖር የሚችል፣ አጭርና ጥቅጥቅ ያለ ሆኖ እንደሃር የለሰለሰ ፀጉር ያለው፣ እንደ አሳ፣ እንቁራሪት፣... ያሉትን እንስሳት የሚመገብ አውሬ።

አቋም "ቆመ" ስር ተመ.

አበለ ግ 1.ዋሸ፣ ቀጠፈ። 2.ሸፈጠ። 3.ፍሬ፣ ምርት አልሰጥ አለ። *መሬቱ አበለ።*

አባይ ቅ ዋሾ፣ ቀጣፊ።

አባይ ሚዛን ስ በትክክል የማይመዝን ወይም ጎደሎውን እንደሙሉ አድርጎ የሚያሳይ ሚዛን።

አባይ ጠንቋይ ስ ሊሆን ወይም ሊደረግ የማይችለውን ይሆናል፣ ይደረጋል እያለ ሰዎችን የሚያታልል፣ አዋቂ ነኝ ባይ ጠንቋይ።

እብለት ስ ውሸት፣ ቅጥፈት።

አስተባበለ ግ የተባለው ነገር ውሸት ነው አለ። *ስለግድያው የተሰራጨውን ወሬ አስተባበለ።*

አበል "በላ" ስር ተመ.

አበልጅ ስ አንዱ የሌላውን ሰው ልጅ ክርስትና በማንሳቱ ምክንያት በመካከላቸው የሚፈጠር የዝምድና አይነት (አንሺውም ሆነ የልጁ ወላጆች እርስ በርሳቸው አበልጅ በመባባል ይጠራራሉ)።

አበምኔት "ምኔት" ስር ተመ.

አበረ ግ አንድ ሆነ፣ ተባበረ።

አብሮ በአንድ ላይ፣ በአንድነት ሆኖ። *ከእሱ ጋር አብሮ ይሰራል።*

አብሮ አደግ ስ በአንድ አካባቢ አብሮ ያደገ የእድሜ እኩያ።

አባሪ ስ በተጨማሪ መረጃነት ወይም ማረጋገጫነት ከዋናው ጉዳይ ጋር ተያይዞ የሚቀርብ የፅሁፍ ማስረጃ።

አባሪ ተባባሪ ቅ አጋዥ፣ ረዳት በተለይ በወንጀል ድርጊት ላይ።

ተባበረ ግ ተጋዘ፣ ተረዳዳ፣ በህብረት ሆነ።

ተባባሪ ስ በሃሳብ፣ በስራ፣... አጋዥ፣ ረዳት።

ትብብር ስ 1.አንድነት፣ ህብረት። 2.መረዳዳት፣ መተጋገዝ።

አስተባበረ ግ አንድ የሆነ ጉዳይን እንዲያከናውኑ የተለያዩ ወገኖች አንድ ላይ እንዲሆኑ አደረገ፣ አሰባሰበ።

አስተባባሪ ቅ 1.አንድ የሆነ ጉዳይ እንዲያከናውኑ የተለያዩ ወገኖች አንድ ላይ እንዲሆኑ የሚያደርግ፣ የሚያሰባስብ፣ የሚያቀናጅ። 2.የስራ ሃላፊ፣ ተቆጣጣሪ።

አበሰ ግ 1.ጠረገ፣ ወለወለ። *ጠረጴዛውን በጨርቅ አብሰው/አብሺው ስለአለቀ ድስቱን አብሰህ ብላ።* 2.ቀባ። *ፊትህ አመድ መስሏል ቅባት አበስ አድርገው።*

እባሽ ቅ 1.ጥራጊ፣ ትራፊ (የወጥ)። 2.ወጥ የነካው፣ ትራፊ (እንጀራ)።

እብስ አደረገ ግ ሙጥጥ፣ ጥርግ አደረገ።

ተባበሰ ግ ተቀባባ (ሰውነትን በቅባት)።

አበሱዳ ስ ጥቁር አዝሙድ።

አበሳ ስ 1.መከራ፣ ስቃይ፣ ፍዳ። 2.ጥፋት፣ ሃጢአት፣ በደል።

አበስኩ ገበርኩ ሰዎች የሚያስደነግጥ ወይም የሚያስፈራ ነገር ባዩ ወይም በሰሙ ጊዜ ከእንደዚህ አይነት ሰውረን፣ አድነን ለማለት የሚጠቀሙበት አባባል።

አበሻ "ሃበሻ"ን ተመ.

አበቀ^{1} ግ እየመታና እየጠቀጠቀ ከእቃ ውስጥ ከተተ፣ ጨመረ (ለምሳሌ ዱቄትን)።

አበቀ^{2} ግ ወጋ። *በጦር አበቀው።*

አበቀ^{3} ግ የቀጠነ ሊጥን ዱቄት በመጨመር እንዲወፍር አደረገ።

አበቅ ስ 1.እብቅ። 2.እክክ፣ ድርመን።

አበበ ግ 1.አበባ አወጣ። 2.አማረ፣ ደመቀ፣ አሸበረቀ።

አበባ ስ 1.ማንኛቸውም የእፅዋት አይነቶች የፍሬ ጊዜያቸው ሲደርስ ፍሬያቸውን የሚመሰርቱበት፣ ከእንቡጥ ውስጥ ተሸልቅቆ የሚወጣና እንደ እፅዋቱ የዝርያ አይነት የተለያየ ቀለም፣ ቅርፅና መጠን ያለው የእፅዋቱ አካል፣

የአፅዋቱ ፍንድ። 2.አይን የሚስብና ለጌጥ የሚሆን ውብ ቀለም ያለው አበባ የሚያወጣ የተክል አይነት።

አበባ ምንጣፍ ስ በአበባ ንድፍ ወይም ምስል የተጌጠ የምንጣፍ አይነት ወይም ስጋጃ።

አበባ ጎመን ስ የአበባ ቅርፅ ያለውና ቅጠሉ ጥቅል ጎመን የሚመስል፥ መጠኑ ትንሽ የሆነ የጎመን አይነት።

አበባ ጎመን

የአበባ ማስቀመጫ ስ ለጌጥ ሲባል አበባ ተቆርጦ የሚቀመጥበት፥ የተለያዩ ቅርፅና መጠን ያለው፥ ከብርጭቆ ወይም ከሸክላ ወይም ከፕላስቲክ፥... የሚሰራ እቃ።

የአበባ እህል ስ አበባው ጎላ ብሎ የሚታይ እንደ ባቄላና አተር ያለ የእህል አይነት።

የአበባ ጉንጉን ስ ክብ ወይም ሌላ አይነት ቅርፅ ባለው ነገር ላይ ዙሪያውን አበባ በመሰካት የሚዘጋጅና በአንድ ውድድር (ሩጫ፥ ኳስ ጨዋታ፥...) ተወዳድሮ ላሸነፈ ወይም የጀግንነት ስራ ለሰራ፥... የሚበረከት ወይም በቀብር ስነስርአት ጊዜ በመቃብር ላይ የሚደረግ አበባ።

አበተ ግ አሰረ።

ማበቻ ስ ለማሰሪያነት የሚያገለግል እንደ ገመድ ያለ ማንኛውም ነገር።

አበኑስ ስ ትንሽ ጣባ ወይም ቆሬ።

አበክሮ "***በከረ**" ስር ተመ.

አበው (ነጠ.ቁ.**አብ**) ስ የቀድሞ ሰዎች፥ ሽማግሌዎች፥ አባቶች።

አበይት "**አቢይ**"ን ተመ.

አበደ ግ 1.አእምሮው ተቃወሰ፥ የአእምሮ ህመምተኛ ሆነ። 2.በጣም ተናደደ። 3.ወደደ፥ አፈቀረ። 4.ከገደብ ያለፈ ወይም ተገቢ ያልሆነ ድርጊት ፈፀመ።

አበደላት በጣም አፈቀራት።

በ—ያበደ በ—ጥሩ ሆኖ የተሰራ። (ምግብ፥ መጠጥ፥...)። *በቅመም ያበደ ሻይ።*

እብድ ቅ ቀውስ፥ ወፈፌ፥ የአእምሮ ህመምተኛ።

እብድ ቀን ስ ያሰቡት ያልሆነበት ወይም ያልተሳካበትና ትርምስ የበዛበት ቀን።

እብድ ውሻ ስ አእምሮውን የታመመ ውሻ።

እብደት ስ 1.በአእምሮ መታመም ወይም መቃወስ የተነሳ የሚመጣ በሽታ። 2.ከመጠኑ ያለፈ ወይም ተገቢ ያልሆነ ድርጊት።

አሳበደ ግ በጣም አሳመረ፥ አስጌጠ። *ስእሉን አሳብዶ ሰራው።*

አበደም ስ ጠላት፥ ባላጋራ (በነፍስ ግድያ ምክንያት)።

አበገደ ስ ጥንታዊ የግእዝ ቋንቋ ፊደል ተራ።

አቢጋዝ ስ "ጦር" ስር "የጦር አቢጋዝ"ን ተመ.

አበጠ[1] ግ 1.ተነፋ፥ ተነረተ (ሰውነት)። 2.ተጀነነ፥ በትእቢት ተወጠረ። 3.አካረረ።

አባጣ ቅ አበጥ ያለ ወይም እብጠት ያለበት። 2.ጉብታ ወይም ከፍታ።

አባጣ ጎባጣ ቅ ወጣ ገባ ወይም ያልተስተካከለ።

እበጥ ስ እባጭ።

እባጭ ስ እንደ እባጢ ሆኖ ሰውነት ላይ የሚወጣ የበሽታ አይነት።

እብጠት ስ በህመም ወይም በመመታት ምክንያት የሰውነት ማበጥ፥ መነረት።

አበጠ[2] ግ አወከ፥ ረበሸ፥ በጠበጠ። *ልጁ አልተኛም ብሎ ሊያብጠን ዋለ።*

አቡነ ዘለብ ስ የበቅሎን ወይም የፈረስን የጭራ ስር ከኮርቻ ጋር የሚያያዝ ጠፍር(ስእሉን ኮርቻ ስር ተመ.)።

አቡን ስ የጳጳስና የኤጲስ ቆጶስ የወል መጠሪያ።

አቡነ— የጳጳስና ወይም የኤጲስ ቆጶስነት ስልጣን ካላቸው የቤተክርስቲያን ሰዎች ስም ጋር እየተጣመረ ለመጠሪያነት የሚያገለግል የማእረግ ስም። *አቡነ ሰላማ።*

አቡጀዲ ስ በፋብሪካ የሚሰራና ነጣ ያለ ቀለም ያለው የጨርቅ አይነት።

አቡጊዳ ስ በቤተክህነት ትምህርት ቤት ከሆሄ ቀጥሎ ከመልእክተ ዮሃንስ በፊት የሚሰጥ የፊደል ትምህርት።

አቢይ (ብ.ቁ.**አበይት**) ቅ ትልቅ፥ ዋና።

አቢይ ሃረግ ስ (ሰዋ.) የአንድን አረፍተ ነገር ዋና ግስ ወይም ማሰሪያ አንቀፅ የያዘ ሃረግ።

አቢይ ፆም ስ ሁዳዴ፥ ፆመ ኢየሱስ፥ ፆመ አርበአ።

አባ[1] ስ ከስም ጋር እየተጣመረ ወይም ለብቻው በመሆን ወንድ መነኩሴን ለመጥራት የሚያገለግል ቃል። ትርጓሜውም አባት ማለት

ነው።

አባሆይ ስ ወንድ መነኩሴን ለመጥራት የሚያገለግል ቃል።

አባ² ግ ሸሸገ፣ ደበቀ። *ሆድ ያባውን ብቅል ያወጣዋል።*

አባ— 1.የ— ባለቤት፣ የ—ጌታ እንደ ማለት ሲሆን በአብዛኛው ለፈረስ ከሚወጡና ጀግንነትን ከሚገልጡ ስሞች ጋር በማጣመር የፈረሱን ባለቤት በፈረሱ ስም ለመጥራት የሚያገለግል የቅፅል ስም። *አባታጠቅ /አባበዝብዝ/ አባዳኘው/አባጠቅል ...* ። 2.የአንድን ሰው ጠባይ፣ ስራ፣... ለመግለፅ ከጠባዩ ወይም ከስራው ቀድሞ የሚገባ የቅፅል ስም። *አባመስጠት = ቸር፣ ለጋስ።*

አባሆይ "አባ¹" ስር ተመ.

አባለዘር ስ 1.የወንድ ብልት ወይም ሃፍረተ ስጋ። 2.የወንድ ወይም የሴት ብልት።

የአባለዘር በሽታ ስ አብዛኛውን ጊዜ በግብረ ስጋ ግንኙነት ሳቢያ የሚተላለፍ እንደ ቂጥኝና ጨብጥ ያለ በሽታ።

አባል ስ የቡድን፣ የማህበር፣ የድርጅት፣... አካል ወይም ተሳታፊ። *የፓርቲ አባል።*

አባሎ ስ በቆላና በወይና ደጋ የሚበቅል፣ ፍሬው ለጠላና ለወተት እቃ ማጠኛ የሚያገለግል የእፅዋት አይነት።

አባሬ "አበረ" ስር ተመ.

አባር ቅ ድርቅ፣ ቦና።

አባሰንጋ ስ የከብት በሽታ አይነት።

አባበለ "*ባበለ" ስር ተመ.

አባባ "ባባ¹" ስር ተመ.

አባባ ስ 1.አባቴ ለማለት ልጆች አባታቸውን የሚጠሩበት ቃል ወይም የተዘምዶ ስም። 2. ሽማግሌዎች ፥ አዛውንቶች የሚጠሩበት የአክብሮት ቃል ወይም ስም።

አባተ¹ ግ አየለ፣ በረታ፣ የበላይ ሆነ፣ በቁጥጥር ስር አደረገ፣ አሸነፈ።

አባተ² "ባተ" ስር ተመ.

አባት ስ ፆታው ተባእታይ የሆነ ትልቅ ወንድ ወይም ወንድ ወላጅ የሚጠራበት የወል ስም።

ያባት ነው ደንብ፣ ወግ፣ ስርአት ነው። *ወላጆችን መርዳት ያባት ነው።*

አባወራ ስ የቤተሰብ ሃላፊ፣ አስተዳዳሪ (ወንድ)።

አባዜ ስ 1.መጥፎ ቁራኛ፣ ሞገድ፣ እልክ። 2.ችግር፣ እንቅፋት።

አባያ ቅ 1.በደንብ የማያርስ፣ የሚለግም (በሬ)። 2.ልግመኛ፣ አልምጥ።

አቧዬ ስ ልጅ አባቱን የሚጠራበት ቃል ወይም የተዘምዶ ስም።

አባይ "አበለ" ስር ተመ.

አባጀሆኝ ስ በበጋ ወራት ሳይደርቅ ለአመት ያህል ጥቅም የሚሰጥ የጎመን አይነት።

አባጎንዳ ስ አሚናፗ ሳሊበላ።

አባጣ "አበጠ" ስር ተመ.

አባጨጓሬ ስ 1.የሚኮሰኩስና ጨፍራራ ፀጉር ያለው ትል። 2.(ዘይ.) ፀባዩ አስቸጋሪ የሆነ (ሰው)።

አቤት 1.ወንድ ሲጣራ "አለሁ፥ ምን ልታዘዝ፣..." ለማለት በስም የተጠራው ሰው ለጠራው የሚያሰማው ትህትናን የተላበሰ የመልስ ቃል። 2.የሚያስደንቅ ወይም የሚያስገርም ነገር ሲታይ ወይም ሲሰማ አድናቆትን ወይም መገረምን ለመግለፅ የሚነገር ቃል። *አቤት! ምን ያምራል።*

አቤት አለ ግ አቤቱታ አቀረበ ወይም አሰማ፣ አመለከተ።

አቤት ባይ ቅ አቤቱታ የሚያቀርብ።

አቤቱታ ስ በደል ደርሶብኛል የሚል ሰው በደሉን ለበላይ ባለስልጣን ወይም ለሚመለከተው ለሌላ ሰው በቃል ወይም በፅሁፍ የሚያቀርበው ፍሬ ሃሳብ፣ ክስ፣ በደል።

አቤቱታ አቀረበ/አሰማ አቤት አለ።

አብሳሊት ስ አለብላቢት።

አብራክ

ከአብራኬ የወጣ/የተከፈለ[ልጅ] የወለድኩት ልጅ።

አብሲት ስ እንጀራን ለማለስለስና ለማሳመር ሲባል የቡኩ ሊጥ ላይ የሚጨመር የፈላ ውሃ ወይም ከቡኩው ተቀንሶ በፈላ ውሃ የሚበጠበጥ ሊጥ።

አብሲት ጣለ አብሲት አዘጋጅቶ በሊጥ ላይ ጨመረ።

አብሽ ስ ፍሬው አነስ ያለና መልኩ ቢጫ የሆነ፣ በጣም የሚመር፣ ተፈጭቶና ተበጥብጦ የሚጠጣ ወይም በቅመምነት የሚያገለግል የቅመም አይነት። ቅጠሉም አብሽ ይባላል።

አብሽሉ ስ ከዳጉሳ ወይም ከበቆሎ፣... የሚዘጋጅ የጠላ ቂጣ።

አብሾ ስ ፍሬውን ወይም ቅጠሉን ሲበሉት ለተወሰነ ጊዜ የሚያሰክር ወይም አእምሮ የሚለውጥ አደንዛዥ እፅ።

አብሿም ቅ 1.አብሾ ጠጥቶ አእምሮው የተነካ፣ ወፈፍተኛ። 2.ትንሽ ጠጥቶ የሚሰክር፣ ሰካራም።

አብነት¹ ስ ምሳሌ፣ አርአያ።

አብነት² ስ1. ከተለያዩ ስራስሮችና ቅጠላ ቅጠሎች የሚቀመምና የሚደገምበት የባህል

መድሃኒት፡፡ 2.የጠለቀ ትምህርት ያለውና አዋቂ መምህር፡ ምስክር፡፡ *አለቃ እገሌ የብሉይና የሃዲስ ኪዳን ትርጓሜ አብነት ነበሩ፡፡*

አብዛኛው "ብዛ" ስር ተመ.

አብዬ ስ ልጅ አባቱን አባዬ፡ አባቴ ለማለት ወይም አንድ ሰው ታላቁን ወይም ሽማግሌዎችን ተአዛውንቶችን የሚጠራበት የተዛምዶ ወይም የአክብሮት ቃል ወይም ስም፡፡

አብዮት ስ በአንድ ነገር ክስተት ወይም ሂደት ውስጥ ያሉ ቅራኔዎች ተካረው ከፍተኛ ደረጃ ላይ ሲደርሱ የሚፈጠር መሰረታዊ ለውጥ፤ አዲስ ከፍተኛና የተሻለ ነገር፡ ክስተትና ሂደት ወይም አስተሳሰብና እውቀት የሚከሰትበት፡፡

አቦል [**ቡና**] ስ በአገር ባህል የቡና አፈላል ልማድ በመጀመሪያው ዙር ላይ ተፈልቶ የሚቀዳው ቡና፡፡

አቦሊ ቅ የነጭና የቀይ ቀለም ቅይጥ መልክ ያለው (ጤፍ፡ አፈር፡...)፡፡ *አቦሊ መሬት፡*

አቦሬ ስ አፉ ሰፊ የሆነ ትልቅ ሸክላ፡፡

አቦሬ አፍ (ስድብ) ቅ 1.አፉ ትልቅ ወይም ሰፊ የሆነ (ሰው)፡፡ 2.(ዘይ.) ሳያስብና ሳያመዛዝን እንዳመጣለት የሚናገር (ሰው)፡፡

አቦስጥ ስ መላምት፡ ግምት፡፡ *ፈተናውን በአቦስጥ ሰራሁት፡*

አቧራ (**አዋራ**) ስ ደቃቅ አፈር ወይም ትቢያ፡፡

አቧራማ ቅ አቧራ የበዛበት (ቦታ)፡፡

አተላ ስ 1.ጠላ ተጠምቆ ካለቀ በኋላ ከስሩ የሚቀረው ዝቃጭ፡፡ 2.የማንኛውም ፈሳሽ ነገር ዝቃጭ፡፡

አተመ ግ 1.በማተሚያ መሳሪያ ፃፈ፡፡ 2.በማህተም ረገጠ ወይም ማህተም አደረገ፡፡ 3.አሸገ፡ ዘጋ (ደብዳቤን)፡፡

ህትመት ስ በማተሚያ መሳሪያ አማካይነት ፅሁፍን የማተም ስራ፡፡

ማህተም ስ 1.በአንድ መስሪያ ቤት፡ ድርጅት ወይም ማህበር ውስጥ ለሚከናወኑ ተግባራት እንደ መለያ የሚሆነው የመስሪያ ቤቱ፡ የድርጅቱ ወይም የማህበሩ ስም ወይም አርማ በላዩ ላይ የተቀረፀበትና ቀለም ላይ እየተረገጠ ምልክቱን በደብዳቤዎች፡ በማስታወቂያዎች፡... ላይ ለማስቀመጥ የሚያገለግል ከእንጨት ወይም ከብረት፡ ... የሚሰራ ምልክት ማድረጊያ የፅህፈት መሳሪያ፡፡ 2.ከላይ በተጠቀሰው መሳሪያ በመጠቀም በደብዳቤዎች፡ በማስታወቂያዎች፡ ... ላይ የሚቀመጥ ምልክት፡፡

ማተሚያ ስ ልዩ ልዩ ፅሁፎችንና ቅርፆችን አትሞ ወይም ቀርፆ የሚያወጣ መሳሪያ፡፡

ማተሚያ ቤት ስ ልዩ ልዩ ፅሁፎችን በመፅሄት፡ በመፅሃፍ፡... መልክ በማተሚያ መሳሪያ እያተመ የሚያወጣ ድርጅት፡፡

አታሚ ቅ አሳታሚ፡፡

እትም ስ በአንድ ዙር ታትሞ የሚወጣ የአንድ መፅሃፍ፡ መፅሄት፡ ጋዜጣ፡ ... ቅጂ በሙሉ፡፡ *አንደኛ እትም፡ ሁለተኛ እትም፡...፡፡*

ታተመ ግ 1.ማተሚያ ቤት ገብቶ በማተሚያ መሳሪያ ታትሞ (ተፅፎ) ወጣ (መፅሃፍ፡ መፅሄት፡ ጋዜጣ፡...)፡፡ 2.ታሸገ፡ ተዘጋ፡፡

አሳተመ ግ መፅሃፍ፡ መፅሄት፡ ጋዜጣ፡... አዘጋጅቶ ለህትመት አበቃ አትሞ አወጣ፡፡

አሳታሚ [**ድርጅት**] ስ በሌላ አካል የሚቀርቡ ረቂቅ መፃህፍትን፡ መፅሄቶችን፡ ጋዜጦችን፡... ሃላፊነት በመውሰድ አዘጋጅቶ እንዲታተሙ የሚያደርግ ድርጅት፡፡

አተረ ግ እንደ አተር ድድር ወይም ጥጥር ብሎ አበጠ፡፡

አተር ስ ድቡልቡል ፍሬዎቹ በሽፋን ውስጥ ድርድር ብለው የሚገኙና አገዳው እንደ ሃረግ ሆኖ የሚያድግ የአበባ እህል፡፡

አተሬ [**ቂጥኝ**] ስ የአተር ፍሬ መስሎ የሚወጣ የቂጥኝ አይነት፡፡

እትራት ስ እንደ አተር ፍሬ ያለ እብጠት፡፡

አተበ ግ እትብት ቆረጠ፡፡

አታቢ ቅ እትብት የመቁረጥ እውቀት ያለው ሰው፡፡

እትብት ስ ህይወት ያለው ፍጡር በእናቱ ማህፀን ውስጥ ባለበት ጊዜ፡ ከእናቱ ምግብ የሚያገኝበት ከእምብርቱ ጋር የተያያዘ የምግብ ማመላለሻ አካል፡፡

ታተበ ግ እትብቱ ተቆረጠ፡፡

አተተ ግ በዝርዝር አብራራ፡ ተነተነ (በፅሁፍ፡ በቃል)፡፡

ሃተታ (**አተታ**) ስ 1.በአንድ ሃሳብ ላይ በዝርዝር የሚቀርብ ማብራሪያ፡፡ 2.ዝርዝር ወሬ፡፡ *በአጭሩ ተናገር ሃተታ አታብዛ፡*

ታተተ ግ ተብራራ፡ በዝርዝር ቀረበ፡፡

አተካረሰ "ተካረሰ" ን ተመ.

አተካራ ስ ንዝንዝ፡ ጭቅጭቅ፡፡

አቴች ስ ለባህል መድሃኒትነት የሚጠቀሙበት አነስተኛ የእፅዋት አይነት፡፡

አታሚ "**አተመ**" ስር ተመ.

አታሞ ስ አነስተኛ ከበሮ፡፡

አታቢ "**አተበ**" ስር ተመ.

አታክልት "**ተከለ**" ስር "አትክልት"ን ተመ.

አቴቴ ስ የዛር አይነት፡፡

አቴና ስ ከቀርከሃ ወይም ከሸንበቆ እንደ ቅርጫት

እየተቃጣ የሚሰራ የቤተ ክርስቲያን ወይም የቤተ መንግስት ወለል ንጣፍ፤ ይህ ንጣፍ ይሰራ የነበረው የቤት ወለል በግንብ፣ በሲሚንቶ፣ ... በማይሰራበት ጊዜ ነበር።

አትላስ ስ የተለያዩ የመልክአ ምድር ካርታዎች ብዛት ያሉበት መፅሃፍ።

አትሌቲክስ ስ ሩጫ፣ ዝላይና ውርወራን የሚያጠቃልል የስፖርት አይነት።

አትሌት ስ በሩጫ፣ በዝላይና በውርወራ የሰለጠነ ስፖርተኛ።

አትሮንስ ስ ባለ ስድስት ወይም ባለ አራት እግር ተደርጎ ከእንጨት ወይም ከብረት የሚሰራና መፅሃፍ እላዩ ላይ ተዘርግቶ ለማንበቢያነት የሚያገለግል ብዙ ጊዜ በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚገኝ እቃ።

አትክልት "ተከለ" ስር ተመ.

አትኳር ስ እንደ አንፋር ያለ በወይና ደጋ የሚበቅል የእፅዋት አይነት።

አቶ ቅ እንደ ደጃዝማች፣ ፊታውራሪ፣ ...ያለ የማዕረግ ስም ከሌላቸው ትላልቅ ወንዶች ስም ጋር እየተጣመረ የሚነገር የአክብሮት ስም ወይም መጠሪያ። *አቶ ታምራት፣*

አቶሚክ (አውቶሚክ) ቦንብ ስ ከአቶም የሚሰራ ቦንብ።

አቶም ስ የአንድ ቁስ አካል የመጨረሻው ትንሹ ክፍል ወይም ንጥረ ነገር።

አቶሳል ስ ጠቆር ያለ የስንዴ አይነት።

አቻ ቅ እኩያ፣ በእኩል ደረጃ የሚገኝ።

አነር ስ ምድቡ ከድመትና ከነብር ወገን የሆነ፣ አካሉ ወርቅማ ሆኖ ጥቁር መቅጠቆና ሽንትሮች ያሉበት፣ እንደአይጥ፣ እንሽላሊት፣ ዶሮ፣ ... ያሉትን የሚመገብ የዱር አውሬ(ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።

አነሰ ግ 1.ተነሰ፣ ጎደለ (መጠን፣ ብዛት)። 2.ዝቅ አለ (ደረጃ፣ ጥራት)።
ቢያንስ በትንሹ። *ለልብሱ ቢያንስ መቶ ብር ያስፈልገዋል።*

አናሳ ቅ ትንሽ።

አነስተኛ ቅ ትንሽ የሆነ፣ ዝቅተኛ (በብዛት፣ በመጠን፣ በደረጃ)።

ታናሽ (ብ.ቁ.ታናናሽ) ቅ 1.በእድሜ ከሌላው የሚያንስ ወይም ትንሽ የሆነ። 2.ትንሽ እህት ወይም ወንድም። *ታናሼ በቁመት ትበልጠኛለች።* 3.ከስጋ ብልቶች አንዱ የሆነው የበሬ የፊት እግር።

ትንሽ (ብ.ቁ.ትንንሽ፣ ትናንሽ) ቅ 1.የነሰ፣ ዝቅ ያለ (በእድሜ፣ በመጠን፣ በማዕረግ)። 2. ጥቂት።

ትንሽ ሰው ነው ወራዳ፣ ባለጌ ነው።

ትንሽ ጣት ስ ከቀለበት ጣት ጎን በዳር በኩል የምትገኝ፣ ከሌሎቹ ጣቶች አጠርና ቀጠን ያለች ጣት(ስእሉን እጅ ስር ተመ.)።

አነቀ ግ 1.ጉሮሮን በመያዝ፣ በማሰር፣ ... መተንፈስ ከለከለ። 2.በጉሮሮ ውስጥ ተወተፈ፣ አልወርድ አለ (ምግብ)። 3. አድብቶ ወይም ተደብቆ በድንገት ያዘ። *ሌቦቹ በጨለማ ሰው እያነቁ ይዘርፋሉ።*

ማነቆ ስ 1.በተጠመደ ቀንበር ውስጥ ገብቶ በበሬው አንገት ሥር የሚውልና በሬው እንዳይፈለቅቀው ወዲያና ወዲህ እንዳይንቀሳቀስ የሚያግድ የእርሻ እቃ (ስእሉን ሞፈር ስር ተመ.)። 2.እንቅፋት። *ስራው እንዳይቀጥልበት ቢሮክራሲው ትልቅ ማነቆ ሆነበት።*

ታነቀ ግ 1.በገዛ እጁ ራሱን በገመድ ወይም በቀበቶ፣ ... አነቀ ወይም ሰቀለ። 2.በጉሮሮው ውስጥ በተወተፈ ወይም አልወርድ ባለ ምግብ፣ ... የተነሳ መተንፈስ አቃተው።

ተናነቀ ግ 1.ታገለ። 2.ሊወጣ ፈለገ (ትውኪያ)።

ትንቅንቅ ስ 1.ግፊያ፣ ትርምስ። 2.ትግል።

አነበ ግ ንብ አረባ።

ንብ በፊደል ተራው ተመ.

አነባ ግ አለቀሰ፣ እንባ አፈሰሰ።

እንባ (እምባ) ስ ሲለቀስ ወይም አይን ላይ ጉዳት ሲደርስ ከአይን የሚወጣ ውሃ መሳይ ፈሳሽ።

በእንባ ተለያዩ ተላቅሰው ተለያዩ።

በእንባ ተራጩ በጣም ተላቀሱ።

እንባ በእንባ ሆነ በጣም አለቀሰ።

እንባ አነቀው (ተናነቀው) ከውስጥ ፈንቅሎ በወጣ ሃዘን፣ ብስጭት ምክንያት እንባው ተንቆረዘዘ፣ ለማልቀስ ወይም ለማንባት ተቃረበ።

እንባ እንባ አለ ልቡ በጣም አዘነው።

እንባ እንባ አለው እንባው መጣበት።

አልቅስ የሚል ስሜት ያዘው።

እንባው ረገፈ እንባው ፈሰሰ።

እንባው ቅንዝፍ ቅንዝፍ አለ እንባው ዱብ ዱብ አለ፤ ፈሰሰ።

እንባውን አወረደው አለቀሰ፤ አነባ።

እንባውን ጠጣ የመጣበትን እንባ እንደምንም ብሎ እንዳይፈስ አደረገው።

እንባ አስመጪ ጋዝ የሚያስለቅስ ወይም እንባ የሚያስመጣ የጋዝ ጭስ(ብዙ ጊዜ ሰልፍ ወይም ግርግር ለመበተን የሚያገለግል)።

እንባ አድርቅ ስ 1.ለቀባሪ የሚቀርብ ንፍሮ። 2.ድምፅ መጥፎ አልቃሽ። 3.(ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ከሬሳ ጋር ወደ ቤተክርስቲያን የሚወሰድ እንጀራና ጠላ።

እንባ ጠባቂ ስ ፍርድ አስተካካይ፤ እውነተኛ ዳኛ፤ ለድሃ ተቆርቋሪ የሆነ ሹም።

አነባበሮ "ነበረበረ" ስር ተመ.

አነከሰ ግ አነከሰ።

አንካሳ ቅ አንካሳ።

አነከሰ ግ በህመም ወይም በሌላ ጉዳት የተነሳ አንድ እግሩ በደንብ ሳይረግጥ አንደኛው ብቻ በደንብ እየረገጠ ተራመደ።

አንካሳ ቅ 1.በህመም ወይም በሌላ ጉዳት የተነሳ በአንድ እግሩ ብቻ በደንብ እየረገጠ የሚሄድ፤ ሽንካላ። 2.ያልተሟላ፤ ያልተስተካከለ (ሃሳብ፤ ስራ፤ ...)።

የአንካሴ የወላንሴ አንድ እግርን በማጠፍ በሌላው (በሁለተኛው) እግር እየዘለሉ በመሄድ የሚጫወቱት የልጆች ጨዋታ።

አስነከሰ ግ አንካሳ አደረገ።

አነገረ ግ ያልበሰለን የኮሽም ወይም የቅሞ ፍሬ መሬት ውስጥ ቀብሮ እላዩ ላይ እሳት በማንደድ እንዲበስል አደረገ።

አነገበ ግ 1.ተሸከመ፤ ያዘ። 2. አነገተ።

አነገተ ግ የአንድን እቃ ማንገቻ በትከሻ ወይም በአንገት ላይ በማድረግ እቃውን ተሸከመ፤ አነገበ፤ አንጠለጠለ።

ማንገቻ ስ 1.አንድን እቃ በትከሻ ወይም በአንገት ላይ ለማንጠልጠል የሚረዳና ከእቃው ጋር የታሰረ ጠፍር ወይም ገመድ ወይም ሌላ ነገር። 2.በጥብጣብ ወይም በቀበቶ መልክ የሚዘጋጅና በሁለቱም ትከሻዎች ላይ አልፎ በወገቡ ጀርባና ፊት በኩል የሚያያዝ ወይም የሚሰፋ እንደጉርድ ቀሚስና ሱሪ ያሉ የልብስ አይነቶች አካል።

አንጋች ስ የጦር መሳሪያ በመታጠቅ እንደ አሽከር ሆኖ ጌታውን የሚያጅብ ወይም የሚጠብቅ ወታደር።

እንግት ስ የአንጋች የጦር መሳሪያ ወይም ትጥቅ።

አነጎጠ ግ 1.አንቀፈ፤ መታ። 2.በነገር ነካ ወይም ጎነጠ።

እንጉጥ ቅ (ስድብ) ነገር ቆስቋሽ፤ በነገር የሚወጋ።

አነጠነጠ "ነጠነጠ" ስር ተመ.

አነፀ (አነጠ) ግ 1.ጠረበ፤ ላገ። 2.ሰራ፤ ገነባ።

ህንፃ በፊደል ተራው ተመ.

አናፂ (አናጢ) ስ ከእንጨት የሚሰሩ ቤቶችንና እቃዎችን የሚሰራና የሚጠግን ባለሙያ።

ታነፀ ግ 1.ተጠረበ፤ ተላገ። 2.ተሰራ፤ ተገነባ (ህንፃ፤ ሃውልት፤ ...)።

አኒሳ ስ በዳሌ ስጋ አካባቢ የሚገኝና ውስጡ ቅባት ያለው፤ በቀላሉ የሚታኘክ የእንስሳት አጥንት።

አናት ስ 1.መሃል ራስ፤ ጭንቅላት። 2.እንጥል። *ልጁ አናት ወረደው።*

አናቱ (አናቷ) ላይ በትክክል። *ሁለትሰዓት አናቱ ላይ እንገናኝ።*

አናት ላይ ወጣ 1.የበላይ ሆነ፤ በቁጥጥር ስር አደረገ። 2.ባለገ፤ አልታዘዝ አለ፤ ከስነ ስርአት ውጪ ሆነ።

አናናስ ስ አበቃቀሉ እንደ እሬት ሆኖ አነስ ያለና ስሩ ተገምሶ ውስጡ የሚበላ የፍራፍሬ አይነት።

አናደለ ግ 1.ጠገበ፤ ተቤተ። 2.ዘለለ፤ ጨፈረ።

አናጠረ ግ 1.ዘለለ፤ ጨፈረ። 2.ተኩራራ፤ ተቤተ። 3.ከበረ፤ በለፀገ።

አናፂ "አነፀ" ስር ተመ.

አናፈለ "ናፈለ" ስር ተመ.

አናፈረ "ናፈረ" ስር ተመ.

አናፋ ግ 1.ጮሀ፤ ድምፅ አሰማ (አህያ)። 2.በሃይል ጮሀ፤ ደነፋ።

አንሲያጠጠ "ሰጠጠ" ስር ተመ.

አንስታይ "እንስት" ስር ተመ.

አንሶላ ስ ከጥጥ ወይም ከሌላ ለስላሳ ከሆነ ጨርቅ በብርድ ልብስ ቅርፅ ጥንድ ሆኖ የሚዘጋጅና አንደኛው በፍራሽ ላይ የሚነጠፍ ሌላኛው ደግሞ ከብርድ ልብስ ስር የሚለበስ ሳሳ ያለ የሌሊት ልብስ።

አንቀላፋ ግ 1.አንጎላጀ። 2.አሸለበ፤ ተኛ። 3.ፈዘዘ፤ ጃለ፤ ነሆለለ። 4.ሞተ።

እንቅልፍ ስ አይንን በመጨፈንና አካልን በማሳረፍ አእምሮና የስሜት ህዋሳት፤ ... ለተወሰነ ጊዜ የሚያገኙት እረፍት።

እንቅልፉን ለጠጠ ግሩ. እንቅልፍ ወሰደው፥ በደንብ ተኛ።

እንቅልፍ አጣ 1.እንቅልፍ ሳይወስደው፥ ሳይዘው ቀረ። 2.ሃሳብ ገባው፥ በጣም አሰበ።

እንቅልፍ ወሰደው አሸለበ፥ ተኛ።

እንቅልፍ ያዘው ዝ.ከ.

እንቅልፋም ቅ 1.እንቅልፍ የሚያበዛ። 2.ፈዛዛ፥ ነሁላላ ።

አንቀልባ ስ ተፍቆ ከተለፋ ቆዳ የሚሰራና ለህፃን ልጅ ማዘያ የሚያገለግል ስስና ለስላሳ ቆዳ።

አንቀርሻ ስ በጣም የጠቆረ፡ ጥቀርሻ የሚመስል ነገር።

አንቀፅ ስ 1.የአረፍተ ነገር ማሰሪያ፡ ግስ። 2.በፅሁፍ ውስጥ ብዙውን ጊዜ ወደ ውስጥ ገባ ብሎ በአዲስ መስመር የሚጀምርና ብዙ አረፍተ ነገሮችን ሊይዝ የሚችል አዲስ ሃሳብ ወይም ጭብጥ። 3.በህግና ህግ ነክ በሆኑ ሰነዶች ውስጥ በተለያዩ ርእሶች ለሚከፋፈሉ ደንቦች ወይም ድንጋጌዎች እንደመክፈያ ሆኖ የሚያገለግል ርእስ ነገር።

አንቃ (አንቋ) ስ በቆላና በወይና ደጋ የሚበቅል፡ እንጨቱ ክርቻ ለመስራት ወይም በዋና ጊዜ ጀርባ ላይ ታዝሎ ለመንሳፈፍ የሚያስችል፡ እንደ አሱቴ ሲሰበት እሳት ሊፀሀው የሚችልና ቀላልነት ያለው የእፅዋት አይነት።

አንቃር ስ 1. የጉሮሮ የላይኛው ክፍል። 2.እንጥል። 3.የሚበን ልሳን፡ ውልብልቢት።

አንቃር መታው አስታወከው።

አንቃሩን ቅቤ ያልነካው ሲጮህ ወይም ሲያለቅስ ድምፁ የሚሰቀጥጥ።

አንቆላለጨ ግ ሳይሰጥ እያሳየ አጓጓ፡ አጎመጀ።

እንቁልጮልጮህ (እንቁልልጮህ) እንቁልጯልጯሽ።

እንቁልጯልጯሽ (እንቁልልጯሽ) ስ አንድን ነገር እያሳዩ የማጓጓት፡ የማስጎምጀት ድርጊት (የልጆች ድርጊት)።

አንቋ "አንቃ"ን ተመ.

አንቋለጠ (ነውር) ግ 1.ቂጡን ወደፊትና ወደኋላ ወዘወዘ፡ ናጠ (ለወሲብ ድርጊት በሚመስል መልክ)። 2.ነገር ወዲያና ወዲህ ወሰደ፡ አዋሸከ፡ አጣላ።

አንቋሊት ስ እይብ።

አንቋረረ ግ ለቅሶ በሚመስል ድምፅ ጮሀ፤ እንደ እንቁራሪት ያለ ድምፅ አሰማ።

አንበል "አምበል"ን ተመ.

አንበሳ (አምበሳ) ስ 1.ከድመት ወገን ካሉት እንስሳት ሁሉ የሚበልጥ፥ ፀጉሩ ወርቃማ ቢጫ ሆኖ ሆዱ ላይ ትንሽ ነጣ የሚል፡ ረጅም ጅራትና ጋማ ያለው በደን ውስጥ በረጃጅም ዛፎች ስር የሚኖር ሃይለኛና አስፈሪ የሆነ ስጋ በል የዱር እንስሳ። ሴቷ አንበሳ ጋማ የላትም(ስእሉን የዱር እንሰሳ ስር ተመ.)። 2.(ዘይ.) ጀግና፥ ደፋር።

አንበሳ መደብ ስ ሽንት ቤት ወይም ሰገራ ቤት (የንጉስ)።

አንበጣ ስ 1.በበረሃ አሸዋ ውስጥ የሚፈለፈልና ሳር፡ ቅጠልና ሰብል የሚበላ፡ በክንፍ የሚበር የነፍሳት አይነት። 2.(ስድብ፥ ዘይ.) ሆዳም፥ ከርሳም፥ በልቶ የማይጠግብ።

አንቡላ "አምቡላ"ን ተመ.

አንብር ስ (ኢ.አ.ተ.ቤ) መግቻን ወይም ማቆሚያን የሚያሳይ የዜማ ምልክት ( )።

አንባባ "*ባባ" ስር ተመ.

አንቧቃ ቅ ፈሊ፡ ቡከን፥ ቦቅቧቃ።

አንተ ተው. ስ በስም ምትክ እየገባ ለሁለተኛ መደብ፡ ነጠላ ቁጥርና ተባእታይ ፆታ የሚያገለግል ቃል፤ ተውላጠ ስም።

አንቱ ተው.ስ የሁለተኛ መደብ፥ ነጠላ ቁጥር የአክብሮት መጠሪያ።

አንቱታ ስ አንቱ ማለት፡ የአክብሮት አጠራር ወይም አነጋገር።

አንቴና ስ ለሬዲዮ ወይም ለቴሌቪዥን ድምፅንና ምስልን ከአየር ተቀብሎ የሚያስተላልፍ ሽቦ መሰል መሳሪያ።

አንቺ ተው.ስ በስም ምትክ እየገባ ለሁለተኛ መደብ ነጠላ ቁጥርና አንስታይ ፆታ መጥሪያ የሚያገለግል ቃል፤ ተውላጠስም።

አንከሊስ ስ 1.ኩፍኝ። 2.ደካማ፡ አቅመቢስ፥ ከሳሳ።

አንከርት "እንክርት"ን ተመ.

አንካላ "አነከለ" ስር ተመ.

አንካሳ "አነከሰ" ስር ተመ.

አንካሴ ስ ለመቆፈሪያ ወይም ለመውጊያ እንዲያገለግል መጠነኛ ውፍረት ባለው ዘንግ ላይ የተሰካ ሹል ብረት።

አንካቦ ስ 1.ትልቅ ዋንጫ። 2. (ዘይ.) ትልቅ ወይም ሰፊ እግር (የሰው)። 3. ከሰሌን ወይም ከገሳ የተሰራ የጠላ መያዣ።

አንኬል ስ እንደማቶት ያለና ከብረት ወይም ከሃረግ፥... የሚሰራ ክብ የእቃ ማስቀመጫ።

አንኮሮ

በአንኮሮ በአድናቆት፥ በመገረም።

አንኮ ስ 1.የዝንጀሮ መንጋ፤ ጅር። 2. የዝንጀሮ መጥሪያ ቃል። ቅ 3.(ዘይ.) ቂል፥ ጅል፥ ከርፋፋ።

አንኮላ ስ 1.ለውሃ መቅጃ የሚያገለግል ከወደ ቂጡ በኩል ያለው የቅል ጉማጅ። ቅ 2.(ዘይ.) ሞኝ፣ ቂል፣ እንከፍ።

አንኳር ቅ 1.ያልፈራረሰና አንድ ላይ ተያይዞ ያለ የስኳር፣ የጨው፣... ጓል። 2.ዋና ፍሬ ነገር። *ዝርዝር ውስጥ ሳትገባ የጉዳዩን አንኳር ብቻ ንገረኝ።*

አንኳኳ "ኳ^{1}" ስር ተመ.

አንዠት "**አንጀት**"ን ተመ.

አንደርቢ (አንደርብ) ስ አንድ ሰው የበላበት ቤት እንዲቃጠል ወይም የሚበላው ምግብ ቆሻሻ እንዲነዛበት፣... ያደርጋል ተብሎ የሚታመንበት ድግምት፣ አስማት።

አንደበት ስ ለመናገር የሚያስችል የሰውነት ክፍል፣ ልሳን።

አንደበቱ ተዘጋ ዝም አለ፣ መናገር ተሳነው።

አንደበቱ ተፈታ መናገር ጀመረ (በሆነ ምክንያት ሳይናገር የቆየ)።

አንደበቱን ቆለፈው መናገር ተሳነው ወይም አቃተው (በህመም ምክንያት)።

አንደበተ ልቅም ቅ ቁጥብ።

አንደበተ ርቱዕ ቅ ጥሩ ተናጋሪ፣ ንግግር አዋቂ።

አንደበቱ የረታ ቅ ንግግር አዋቂ።

አንድ ስ 1.የመቁጠሪያ ቁጥሮች መጀመሪያ፣ በአሃዝ ሲፃፍ '፩'፣ '1' ነው። 2.ነጠላ፣ ብቻውን የሆነ። ቅ 3.ማንኛውም። *አንድ ሃገር የራሱን ዳር ድንበር ማስከበር አለበት።*

አንድ ሁለት ተባባሉ 1.ክፉና በጎ ተነጋገሩ፣ ተሰዳደቡ። 2.ተገባበዙ (ለመጠጥ)።

አንድ ሁለት ሲሉ 1.በትንሹ ወይም በጥቂቱ ጀምረው። 2.ቀስ በቀስ፣ ሳይታክቱ።

አንድ ሁለት ያህል ጥቂት ወይም አነስተኛ የሆነ።

አንድ ሃሙስ የቀረው የተጎሳቆለ፣ የከሳ፣ የተጎዳ፣ ለሞት የደረሰ የሚመስል።

አንድ ሆነ 1.ተባበረ፣ ተስማማ። 2.ተመሳሰለ፣ ተቀራረበ (በመልክ፣ በቅርፅ፣...)።

አንድ በለኝ 1.አንድ መልስ ስጠኝ። 2.ጋብዘኝ (መጠጥ)። 3.ገላግለኝ። *ይህን ሰው አንድ በለኝ።*

አንድ በለው 1.ዝም አስብለው፣ መልስ ስጠው፣ አናግረው፣ ጉዳዩን ፈጽምለት። 2.ተው በለው። 3.ምከረው።

አንድስ ያህላል አንዳች ያህላል።

አንድና ሁለት የለውም አያወላውልም፣ የተረጋገጠ ነው።

በአንድ ልብ 1.ባለማመንታት፣ ባልተበታተነ ሃሳብ። 2.በአንድነት፣ በህብረት፣ በአንድ አይነት ሃሳብና ፍላጎት። *ለሃገራችን በአንድ ልብ መስራት አለብን።*

በአንድ ቃል/ድምፅ በተመሳሰለና አንድ አይነት በሆነ አቋም፣ አስተሳሰብ።

በአንድ አፍታ በፍጥነት፣ በቅፅበት።

አንዱ በቃኝ 1.በጣም ሃይለኛና አስከሬ የሆነ (መጠጥ)። 2.(ሽሙጥ) ጥራቱ መናኛ የሆነና ተፈላጊነት የሌለው።

አንድ ለአንድ 1.(ስፖ) በውድድር ጊዜ አንድ አንድ ነጥብ በማግኘት እኩል ለእኩል መሆን። *ሳይሸናነፉ አንድ ለአንድ ተለያዩ።* 2.ብቻ ለብቻ።

አንድ ላይ በጅምላ፣ በጥቅል።

አንድ በአንድ 1.በየተራ፣ በተናጠል። 2.በጠቅላላ፣ አንድ ሳይቀር፣ ሁሉም።

አንድ ቀን 1.ወደፊት ከሚመጡት ቀኖች በአንዱ። *አንድ ቀን እመጣለሁ።* 2.ካለፉት ቀናት መካከል በአንደኛው ቀን። *ባለፈው ወር አንድ ቀን ተገናኝተን ነበር።*

አንድ በቀል መንትያ የሌለው፣ አንድ ትንግት ብቻ የሆነ።

አንድ ነገር ያልተገለፀ ወይም ያልታወቀ ነገር።

አንድ አገር አያሌ፣ ብዙ። *ምግቡን አንድ አገር አገጅሬ በልቻለሁ።*

አንድ እግር ስ አንዲ ነጠላ ተክል ወይም ችግኝ (የበርበሬ፣ የጌሾ)።

አንድ ወርዶ ስ አንዱ አጎንብሶ ሳለ ሌላው ከሃላ እየሮጠ መጥቶ ያጎነበሰውን በመዝለል የሚጫወቱት የልጆች ጨዋታ።

አንድ ጊዜ (አንዴ) ተውሳ 1.ሳይደጋገም፣ ብዙ ጊዜ ሳይሆን። *ደብዳቤ የፃፈልኝ አንድ ጊዜ ብቻ ነው።* 2.ለተወሰነ አጭር ጊዜ ለማለት የሚያገለግል ቃል። *አንዴ ይህን መፅሃፍ ያዝልኝ።*

በአንድ ጊዜ 1.ሳይደጋገም። 2.በፍጥነት፣ ቶሎ። *በአንድ ጊዜ ሳደገ።*

አንድ ፍሬ ትንሽ። *አንድ ፍሬ ቆሎ።*

አንደኛ ቅ 1.ቀዳሚ፣ ፊተኛ፣ መጀመሪያ። 2.በደረጃ ወይም በማእረግ ወይም በጥራት ከፍ ያለ፣ የበለጠ።

አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ስ ከ1ኛ እስከ 6ኛ ክፍል ድረስ ያለው ትምህርት የሚሰጥበት ትምህርት ቤት።

አንዲት ቅ በሴቱ ፆታ የሚጠሩ ስሞችን ተከትሎ የሚገባና አንድ ለማለት የሚያገለግል ቃል። *አንዲት ሴት*።

አንዳች ቅ ምንነቱ ያልታወቀ፣ ያልተለየ፣ ያልተገለጠ (አንድ ነገር)። *አንዳች ነገር በዚህ አለፈ*።

አንዳች አይፈታሽ ምንም ነገር የማይበግረው።

አንዳች (አንድስ) ያህላል ትልቅ ወይም ግዙፍ ነው።

አንዳንድ 1.ጥቂት፣ መጠነኛ፣ የተወሰነ። 2.በነፍስ ወከፍ አንድ። *ለሁሉም አንዳንድ ሰጣቸው*።

አንዳንድ ጊዜ ተው.ግ አልፎ አልፎ፣ ሁልጊዜ ሳይሆን።

እያንዳንዱ ቅ 1.አንዱ፣ ነጠላው። *የእያንዳንዱ ማንኪያ ዋጋ አንድ ብር ነው*። 2.ማንኛውም። *እያንዳንዱ ሰው ምግብ ማግኘት አለበት*።

አንድም 1.ምንም፣ ማንም። 2.አለዚያ፣ ወይም።

አንድምታ ስ (ሲ.እ.ተ.ቤ.) አንድ መፅሃፍ ሲተረጎም አባባሉን በተለያየ መንገድ አጉልቶና ዘርዝሮ ሚስጢሩን የመተርጎሚያ ስልት።

አንድነት ስ 1.ህብረት። 2.ተመሳሳይነት።

አንድዬ ስ እግዚአብሔር ወይም አምላክ ለማለት የሚነገር ቃል ።

አንዷዷ "ዷ" ስር ተመ.

አንጀት (አንገርት) ስ በጨጓራ ውስጥ የተፈጨ ምግብ የሚተላለፍበት ቀጭን ቱቦ መሰል የሰው ወይም የእንስሳ ውስጣዊ አካል።



አንጀቱ ራስ /ቅቤ ጠጣ የልቡ ደረሰ፣ የፈለገው ነገር ስለሆነለት ተደሰተ።

አንጀቱ ቆሰለ /ከሰለ በጣም ተናደደ።

አንጀቱ ቆረጠ "ሆድ" ስር "ሆዱ ቆረጠ"ን ተመ.

አንጀቱ ቡጭ ቡጭ አለ "ሆድ" ስር "ሆዱ ቡጭ ቡጭ አለ"ን ተመ.

አንጀቱ (ሆዱ) ተቆለፈ 1.ምግብ አልበላህ አለው ወይም አስጠላው። 2.ተቀየመ።

አንጀቱ ተበጠሰ ተስፋ ቆረጠ።

አንጀቱ ነፈረ "ሆድ" ስር "ሆዱ ነፈረ"ን ተመ.

አንጀቱን ቋጥሮ ተርቦና ተጠምቶ፣ ተቸግሮ።

አንጀቱን አለበው ሃይለኛ ተቅማጥ ያዘው።

አንጀቴን በላኝ አሳዘነኝ።

አንጀቴን አራሰው አስደሰተኝ፣ አረካኝ።

አንጀት ራቀው በምግብ እጦት ወይም በበሽታ ምክንያት ደከመ፣ መናገር አቃተው።

ከአንጀት— ከውስጥ በመነጨ ስሜት፣ ከልቡ። *ከአንጀቱ ሳቀ*።

አንጀት የለሽ ቅ ጨካኝ፣ አረመኔ።

የአንጀት ወዳጅ ስ ችግርንም ሆነ ደስታን የሚያካፍሉት የቅርብ ጓደኛ፣ ምስጢረኛ።

አንጃ ስ ከአንድ የፖለቲካ ድርጅት ውስጥ ተገንጥሎ የወጣ የፖለቲካ ቡድን።

አንጃ ግራንጃ ቅ 1.ዝባዝንኬ፣ ትርኪምርኪ። 2.ጭቅጭቅ፣ ንትርክ።

አንጆ (አኞ) ቅ 1.የከሳ፣ ያረጀ (ከብት)። 2.ለማኘክ የሚያስቸግር ጠንካራ ስጋ። 3.(ዘይ.) ሲያገኙትና ሲያነጋግሩት የማይፈልጉት መንቻካ ሰው።

አንገት ስ ጭንቅላትንና ትከሻን የሚያያይዝ የሰውነት ክፍል(ስእሉን ሰውነት ስር ተመ.)።

አንገቱን ደፋ ተከዘ፣ አዘነ፣ ቅስሙ ተሰበረ።

አንገቱን የደፋ ትሁት፣ ታዛዥ፣ ሊታይ ሊታይ የማይል።

አንገቷን የደፋች 1.ጨዋ፣ አይናፋር። 2.ትሁት፣ ታዛዥ፣ ሊታይ፣ ሊታይ የማትል።

አንገት የለውም 1.የነበረበትን ወይም የደረሰበትን ችግር አያስታውስም። 2.የተዋለለትን ውለታ የማይመልስ፣ ውለታ የማይከፍል፣ ውለታ ቢስ ነው።

አንገተ መቃ ረዥም አንገት ያለው።

አንገተ ሰባራ አይን አፋር፣ ትሁት፣ ጭምት።

አንገተ ደንዳና ምክር የማይሰማ፣ ደንታ ቢስ፣ ግድ የለሽ።

ከአንገት በላይ ለይምሰል፣ ከልብ ወይም ከአንጀት ያልሆነ።

የአንገት ልብስ ስ ከመቀነት አጠርና ሰፋ ብሎ ከጥጥ በሸማኔ የምትሰራ፣ በጫፍና በጫፍ

በኩል ጥለት ያላትና ሴቶች ራሳቸውንና ትከሻቸውን የሚሸፍኑባት ልብስ።

የአንገት ማስገቢያ ትንሽ ቤት ወይም ጎጆ። *የአንገት ማስገቢያ ካለህ በቂ ነው።*

የአንገት ወርቅ ስ ከወርቅ የተሰራና በአንገት ላይ የሚደረግ ጌጥ።

አንገትጌ ስ እንደ ሸሚዝ፥ እጀጠባብ፥ ኮት፥ ... ባሉ ልብሶች ላይ በአንገት በኩል የሚውለው የልብሱ ክፍል፤ ክሳድ፤ ኮሌታ።

አንጉዝ ስ ቆሰሉ የዳነ ወይም የሻረ ጠባሳ።

አንጉጥ "አነገጠ" ስር ተመ.

አንጋሬ ስ የደረቀ የፍየል ወይም የበግ ቆዳ።

አንጋች "አነገተ" ስር ተመ.

አንጋፋ ቅ 1.ታዋቂነትና ቀደምትነት ያለው። 2.ታላቅ፥ የበኩር (ለልጅ)። 3.በእድሜ የገፋ፥ አዛውንት።

አንጎል ስ 1.የነርቭ ማእከል በመሆን አስተሳሰብንና ስሜትን የሚቆጣጠር፥ በራስ ቅል ውስጥ የሚገኝና በጣም ለስላሳ የሆነ የሰውነት ክፍል። 2. (ዘይ.) ንፍጥ።

አንጎሉ ዞረ 1.በትክክል መስራት አቃተው ወይም ተሳነው። 2.በጣም ተበሳጨ።

አንጎል ነው ቀውስ፥ እብድ፥ ወፈፌ ነው።

አንጎለ ቢስ ማስተዋል ወይም ማመዛዘን የማይችል፥ ደሉኝታ ቢስ።

አንጎላም (ስድብ፤ ዘይ.) 1.ጅል፥ 2.ንፍጣም።

አንጎራጎረ ግ 1.ለስለስ ባለ ድምፅ ዘፈን ወይም አዜመ። 2.ሃዘኑን፥ ብሶቱን የሚመለከት እንጉርጉሮ አሰማ።

እንጉርጉሮ ስ አንድ ሰው ብቻውን የሚያዜመው የደስታን ወይም የሃዘንን ስሜት የሚገልፅ ለስላሳ ዜማ።

አንጎርባ ስ ሆድ የሚነፋና ቆበር የሚያስደፍቅ የከብት በሽታ።

አንጓ ስ 1.የጣት ወይም የቅልጥም ወይም የአገዳ ክርክራት። 2.በክርክራቱ መካከል ያለ አካል።

አንጡራ ሃብት/ንብረት ስ የጠራ ሃብት፤ አንድ ሰው ጥሮ ግሮ፥ ወዙን አፍስሶ በግሉ ያገኘው ሃብት።

አንጣሪያ ስ እራሱን ችሎ ወደ ላይ መቆም የማይችል የእፅዋት አይነት። *አንጣሪያ ለአንጣሪያ ቢደጋገፍ ተያይዞ ዘፍ።*

አንጣቆ "እንጣቆ"ን ተመ.

አንጥረኛ "ነጠረ[1]" ስር ተመ.

አንጧጧ "ጧ[2]" ስር ተመ.

አንፃር "*ነፀረ" ስር ተመ.

አንፌላ ስ ተቀቅሎ የሞከከ ንፍሮ ወይም ስጋ ወይም ከእነእንቡጡ የተቀቀለ የአተር ወይም የባቄላ እሸት።

አንፋሮ ስ 1.የአንበሳ ጋማ። 2.ኩሪያውን እንደቆብ በራስ ላይ የሚደረግ የአንበሳ ጋማ።

አንፎርሻ ቅ ያልጠራ ወይም የደፈረሰ (ውሃ)።

አንፏሸረ "ፏሸረ" ስር ተመ.

አንፏሻሪ ዝ.ከ.

አኘከ ግ አላመጠ፤ አመነዠከ (ምግብን)።

አይታኘክም ሲበሉት ለጥርስ ያስቸግራል፤ ጠንካራ ነው።

አኛኪ ቅ ተበልቶና ተመጦ የተተፋ፤ ብላቶ።

አኻ—

አኻ አደረገ ግ ቀረጠጠ፤ ነከሰ።

አኾ "አንጆ"ን ተመ.

አእላፍ "እልፍ[1]" ስር ተመ.

አእማድ "አምድ" ስር ተመ.

አእምሮ ስ ሀሊና፤ ናላ።

አእምሮው ላሸቀ ቀድሞ ከነበረበት ደረጃ ወረደ፥ ዝቅ አለ (በአስተሳሰብ፤ በችሎታ)።

አእምሮው ዛገ አእምሮው ደነዘ፤ ደደበ።

አእምሮ ቢስ 1. ደሉኝታ ቢስ። 2. የማያመዛዝን። 3.የማያስተውል።

አከለ[1] ግ ከ—ጋር እኩል፥ ትክክል ሆነ። *ልጁ አባቱን አከለ።*

እኩሌታ ቅ ግማሽ።

እኩል ቅ 1.ግማሽ፤ እኩሌታ። 2.አቻ፤ የማይበላለጥ።

እኩሉ ግማሹ። *እኩሉ ሲዘፍን እኩሉ ያለቅሳል።*

እኩል ለእኩል 1.መሳ ለመሳ። 2.እኩል ነጥብ ወይም ውጤት ያለው።

እኩል በእኩል ግማሽ በግማሽ።

የእኩል የጋራ።

ያህል (ያክል) 1.መጠንን፤ ብዛትን፤ ልክን ለመግለፅ የሚያገለግል ቃል ። *ስምንት ያህል መፅሃፍ አለኝ።* 2. የአንድን ነገር ድርጊት ወይም መጠን ወይም ክብደት፥ ... በማነፃፀር ለመግለፅ የሚገባ ቃል። *ዘመድ የሞተበት ያህል አዘነ።*

ለ—ያህል (ያክል) 1.በብዛት ሳይሆን በመጠኑ ለማለት የሚነገር ቃል። *ለመቅመስ ያህል።* 2.ከልብ ሳይፈልጉ የሚያደርጉትን ነገር ለመግለፅ የሚነገር ቃል። *ለወጉ ያህል።*

—አሳከለ መጠኑ—ን እንዲያክል (እንዲያህል) አደረገ። *በሬ አሳከለ /ቤቱ አሳከለ።*

እኩለ ሌሊት ስ የሌሊት አጋማሽ፤ መንፈቀ ሌሊት።

እኩለ ቀን ስ ቀትር፤ ከቀኑ ስድስት ሰአት፤ ተሲአት።

እኩሌታ ቅ ግማሽ፤ እኩል።

እኩያ ቅ እቻ፡ ተመጣጣኝ ጓደኛ።

ተካከለ ግ እኩል ሆነ፥ ተስተካከለ።

ትክክል ቅ 1.ልክ፡ እውነት፥ ሃቅ፡ እርግጥ። 2.እኩል የሆነ። *ሁለቱ በቁመት ትክክል ናቸው*፡ 3.አኳያ፡ አንፃር። *በዛፉ ትክክል ቆም*። 4.ቀጥ ያለ፡ አብጥ ጎባጣ የሌለው።

ትክክለኛ ቅ እውነተኛ፡ እርግጠኛ።

ተስተካከለ ግ 1.እኩል ሆነ፡ ተመጣጠነ። 2.ተጠረገ፡ ተደለደለ። *መንገዱ ተስተካከለ*፡ 3.ተቆረጠ፡ ተቀመቀመ (ፀጉር፥ ፅድ)። 4.ትክክለኛውን መስመር ያዘ ወይም ተከተለ። 5.ተገቢውን ደረጃ ወይም መጠን እንዲይዝ ተደረገ። *ደመወዜ ተስተካከለልኛል*። 6.ስርአት ያዘ፡ ልክ ወይም ትክክል ሆነ። 7.ታረመ። *ፅሁፉ ተስተካከለ*፡ 8.ተዘጋጀ፡ ተበጃጀ። *ፊቶ ለመንሳት ተስተካከለ*፡ 9.በአንድ ነገር ትይዩ ወይም አንፃር ሆነ።

አስተካከለ ግ 1.እኩል አደረገ። 2.ትክክል አደረገ፡ አረመ። 3.አነጣጠረ። 4.ቀመቀመ፥ ቆረጠ (ፀጉርን፥ ፅድን)። 5.ተገቢውን ደረጃ ወይም መጠን እንዲያገኝ አደረገ። 6.ጠረገ፡ ደለደለ። *መንገዱን አስተካከለ*፡

አከለ² ግ ጨመረ፡ ደረበ። *በሃብት ላይ ሃብት አከለበት*።

አከመ ግ በሽተኛን አይቶና መርምሮ መድሃኒት በመስጠት፥ በመጠገን፡... ጤናው እንዲመለስለት እርዳታ አደረገ።

ሃኪም በፊደል ተራው ተመ.

ሃኪም ቤት "ሃኪም" ስር ተመ.

ህክምና በፊደል ተራው ተመ.

ታከመ ግ ከበሽታው ለመፈወስ ወይም ለመዳን በሃኪም ታይቶና ተመርምሮ የህክምና እርዳታ አገኘ።

ታካሚ ቅ የህክምና እርዳታ ለማግኘት ሆስፒታል ወይም ክሊኒክ የሚገኝ ህመምተኛ።

አሳከመ ግ የህክምና እርዳታ እንዲያገኝ አደረገ።

አከረ¹ ግ አንድ የእርሻ መሬት በተደጋጋሚ ይዘራበት የነበረውን የእህል አይነት በመተውና ሌላ እህል በመዝራት ወይም ምንም ሳይዘራበት ቢያንስ ለአንድ አመት ያህል ቦዝኖ እንዲከርም በማድረግ የራሱን የተፈጥሮ ማዳበሪያ እንዲያዘጋጅ አደረገ።

እከር ስ በተደጋጋሚ ታርሶ በማርጀቱ የተፈጥሮ ማዳበሪያ ለማዘጋጀት እንዲረዳው የአበባ እህል ተዘርቶበት የቆየ የእርሻ መሬት (በተደጋጋሚ የታረሰ መሬት)። *የባቄላ፥ የአተር፥ ... እከር*።

ታከረ ግ በተለያየ ጊዜ የተለያየ ዘር እየተፈራረቀ ተዘራበት (ማሳ፡ እርሻ)።

አከረ² ግ ጠጠረ፥ ደደረ።

አከርካሪ ስ የጀርባ አጥንት።

አከበ ግ ሰበሰበ፡ አጠራቀመ፡ አከማቸ።

አከተ ግ 1.ኮተቱን ጠቀለለ፡ ሰበሰበ። 2.በተወሰነ ቦታ አከማቸ ወይም ሰበሰበ።

እከት ስ ኮተት፡ ቅራቅንቦ።

እከታም ቅ ኮተታም፥ ቅራቅንቧም።

አከቴ (አከት) ስ የጥርስ እድፍ፡ ልማም።

አከከ ግ 1.ደረመን ወይም እከክ የያዘው ሰው በጥፍሮቹ ሰውነቱን ፎከተ፡ ፈገፈገ። 2. (ዘይ.) ተጎሳቆለ፥ ተቆራመደ (በችግር)።

እከክ ስ ደረመን፥ ፎከት።

እከክ ለበሰ እከክ ያዘው ወይም ወረሰው።

እከካም ቅ 1.እከክ፡ ደረመን የወረሰው ወይም የያዘው። 2.(ዘይ፥ ስድብ) ቆርማዳ፥ ደሃ፡ ችጋራም።

ታከከ ግ 1.አካሉን ከሌላ ነገር ጋር በማነካካት ተሻሸ፥ ተፈጋፈገ። 2.ተጠጋ፥ ነካ። *ላሟ የጎሉን እንጨት ታካ አለፈች*፡3. ተሳበበ ተመካኘ።

አሳከከ ግ በላ፡ አስፎከተ፡ እከኩን እከኩን አለ (ገላ)።

አሳከከው እከክ ያዘው፡ በላው።

አስታከከ ግ 1.አስነካ፡ አስጠጋ። 2.አመካኘ፥ አሳበበ።

አኩፋዳ (አቁፋዳ) "አኮፋዳ"ን ተመ.

አካል (ብ.ቁ. **አካላት**) ስ 1.ሰውነት፡ ገላ። 2.ክፍል። *የበላይ አካል*።

ለአካለ መጠን ደረሰ ለጋብቻ ደረሰ።

አካሌ ፍቅሬ፥ ወዳጄ ለማለት የሚጠቀሙበት ቃል።

አካለ ስንኩል (ብ.ቁ.**አካለ ስንኩላን**) ቅ በተፈጥሮ ወይም በሌላ ምክንያት አካሉ የጎደለ (ሰው)።

አካለ ጎዶሎ ቅ ከመወለዱ በፊት ወይም ከተወለደ በሂላ በደረሰበት ጉዳት አካሉ የጎደለ፡ ሙሉ አካል የሌለው።

አካል ማሰልጠኛ ስ ለአካል ብቃት የሚደረግ እንቅስቃሴ፤ስፖርት።

የአካል ጉዳተኛ ስ በተፈጥሮ ወይም በሌላ ምክንያት አካሉ የጎደለ ሰው።

አካርሚኝ "ከረመ" ስር ተመ.

አካኪ ዘራፍ ቁጣን በተላበሰና ከፍ ባለ ድምፅ የሚባል የጀግንነት፡ የወኔ፥... መግለጫ የሆነ የፉከራ ቃል።

አካይስት ቅ ክፉ፡ ከይሲ።

• **አካዴሚ** ስ 1.በተለያዩ የሙያ ዘርፎች ሰዎችን የሚያሰለጥን ከፍተኛ የትምህርት ተቋም። *ጦር አካዴሚ*፡ 2.በተለያዩ የእውቀት መስኮች ላይ ጥናትና ምርምር የሚያካሂድና የተገኙትን

ውጤቶች ጥቅም ላይ ለማዋል፡ ለማስተዋወቅ፥ ለማበልፀግና የእውቀት መስኮችን በሚመለከት ማንኛውንም ሃላፊነት የሚወስድ ተቋም። *የቋንቋዎች አካዳሚ /ሳይንስ አካዳሚ፡*

ኣካፋ ስ የብረት ወይም የእንጨት እጀታ የተዋደደበት፡ የሳይዳ ወይም የማንኪያ ቅርፅ እንዲኖረው ተደርጎ ከብረት የተሰራና ለአፈር፥ ... መዛቂያ የሚያገለግል መሳሪያ።



ኣካፋ

ኣካፋ "*ካፋ" ስር ተመ.

ኣክ

ኣክታ ስ በጉንፋን፥በሳል፥... ምክንያት ከጉሮሮ የሚወጣ እንደ ንፍጥ ያለ ዝልግልግ ምራቅ።

ኣክ ኣለ ግ ኣክታውን ከጉሮሮው ኣወጣ፡ ኣክ እንትፍ ብሎ ተፋ።

ኣክሊል ስ የቤተክርስቲያን ሰዎች ወይም የነገስታት ወገኖች በበአል ቀን በራሳቸው ላይ እንደቆብ የሚደፉት ከብር ወይም ከወርቅ፥ ... የሚሰራ የክብር ወይም የማእረግ ምልክት።



ኣክሊል

ኣክሊል ደፋ በራሱ ላይ ኣክሊል አደረገ።

ኣክላላ "ክለለ²" ስር ተመ.

ኣክምባሉ "ኣክንባሉ"ን ተመ.

ኣክርማ ስ ለሰፌድ፡ ለቆና፡ ለወንፊት መስሪያ የሚያገለግል የሳር አይነት።

ኣክስት ስ የአባት ወይም የእናት እህት።

ኣክታ "ኣክ" ስር ተመ.

ኣክንባሉ (ኣክምባሉ) ስ ከጭቃ ወይም ከቀርከሃ ተሰርቶ እበት የተለቀለቀ የምጣድ መክደኛ፣ ሙሳድ።

ኣክንባሉ

ኣክንባሉ ሰበራ የአራስነት ጊዜዋን ከጨረሰች ሴት ጋር ለመጀመሪያ ቀን የሚደረግ የግብረ ስጋ ግንኙነት።

ኣክፋይ "*ክፈለ" ስር ተመ.

ኣክፌሉት ዝ.ከ.

ኣኮሌ (ኣሆሌ) ስ ከቅል የሚሰራ የወተት ማለቢያ፣ ግራራ።

ኣኮረተ ግ ኣፈራ፡ ፍሬው ትልልቅ ሆነ (ሽንኩርት፡ ድንች፡...)።

ኣኮርባጅ ስ ከጉማሬ ቆዳ የሚሰራ ወፈር ያለ አለንጋ።

ኣኮርዲዮን ስ ሙዚቀኛው በየተራ በጣቱ የሚነካካቸው ከአምስት እስከ ሃምሳ የሚደርሱ የድምፅ መበጫ ቁልፎች ያሉትና በነፋስ ሃይል የሚሰራ ሳጥን መሰል አነስተኛ ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያ(ስእሉን የሙዚቃ መሳሪያ ስር ተመ.)።

ኣኮቴት ስ ለቁርባን የተዘጋጀ ህብስት።

ኣኮኩ "እንኮኩ"ን ተመ.

ኣኮፋዳ (ኣኩፋዳ፥ ኣቁፋዳ) ስ ከቆዳ ወይም ከሰሌን የሚሰራና የቆሎ ተማሪ ምግቡን ወይም እቃውን የሚይዝበት ከረጢት።

ኣኳሿን "ሆነ" ስር ተመ.

ኣኳስ "*ኳሰ" ስር ተመ.

ኣኳሽ "ኳሸ" ስር ተመ.

ኣኳያ ስ 1.ትይዩ፥ ኣፍላግ፥ ፊት ለፊት። ቅ 2. ኣቻ፡ እኩያ።

ኣወረ ግ እውር አደረገ።

እውር ቅ 1.አይኑ የጠፋ፥ ማየት የማይችል፤ አይነ ስውር። 2.(ለድብ፥ ዘይ) ደንባራ፥ ሰምባራ።

እውር እከክ ስ በጣም የሚያሳክክ ሃይለኛ የሆነ ደረመን ወይም እከክ።

እውር የዘራው በየአቅጣጫው የተዝረከረከ፥ የተመሰቃቀለ፡ በወግና በስርአት ያልተቀመጠ።

ታወረ ግ እውር ሆነ።

ኣወቀ ግ 1.ተረዳ፡ ተገነዘበ፡ አስተዋለ። 2.ለየ። *ገና ከሩቁ ሳየው እሱ እንደሆነ አወቅሁ።* 3.ተማረ፡ አጠና። *የአማርኛ ቋንቋ ጠንቅቆ አወቀ።* 4.በግብረ ስጋ ተገናኘ። *አዳም ሔዋንን አወቃት።*

ኣውቆ ሆን ብሎ፡፡ *ሳውቆ ነው የጠፋው፡*

ኣዋቂ ስ 1.በእድሜ የበሰለ፥ ጎልማሳ፡፡ 2.ብልህ፡፡ 3.ጠንቋይ፡፡ 4.ምሁር፡ ሊቅ፡፡

የኣዋቂ ኣጥፊ ቅ ጥፋትነቱን እያወቀ ጥፋት የሚፈፅም፡፡

እውቀት ስ የሰው ልጅ በትምህርት ወይም በልምድ የሚያገኘውና ለማሰብ፡ ለማስተዋል፡ ለመመራመር የሚያበቃው አእምሮአዊ ችሎታ፡፡

በእውቀት በለፀገ አእምሮው በእውቀት ዳበረ፡፡

እውቅ ቅ ዝነኛ፡ ስመጥር፡፡

እውቂያ ስ ትውውቅ፡፡

ታወቀ ግ 1.ዝነኛ ሆነ፡ ስሙ ገነነ፡፡ 2.ተለየ፡፡ *ሌባው እሱ መሆኑ ታወቀ፡* 3.ተገለጠ፡ ይፋ ወጣ፥ ገሃድ ሆነ፡፡

መታወቂያ[ወረቀት] ስ ለቀበሌ ነዋሪዎች፡ ለመንግስት መስሪያ ቤት፡ ለድርጅት፡ ... ሰራተኞች መለያ እንዲሆን የባለቤቱ ፎቶና አስፈላጊው መረጃ ተፅፎበት የሚሰጥ ካርድ ወይም ወረቀት፡፡

ታዋቂ ቅ ስመጥር፡፡

ተዋወቀ ግ በፊት ከማያውቀው ሰው ጋር ስምና አድራሻ ተገላለፀ፡ ተጨዋወተ፡ ሃሳብ ተለዋወጠ፡፡

ትውውቅ ስ ቀደም ብሎ ከማያውቁት ሰው ጋር ስም፥ አድራሻ፡... መለዋወጥ፥ ግንኙነት፥ ጭውውት ማድረግ፡፡

ኣሳወቀ ግ 1.ገለፀ፡ አስረዳ፡፡ *ጉዳዩን ለበላይ ባለስልጣን ኣሳወቀ፡፡* 2. ይፋ አደረገ፡፡ *ወራሽ መሆኑን በጋዜጣ ኣሳወቀ፡*

ኣስታወቀ ግ 1.አሳወቀ፡፡ 2.ታየ፡ ግልፅ፡ ጉልህ ሆነ፡፡ *ተደጋግሞ ቢታጠብም ቀለም ነክቶት እንደነበረ ኣስታወቀ፡*

ማስታወቂያ ስ የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም ድርጅት ለመግለፅ ወይም ለማስተላለፍ የፈለገውን ነገር ለፎ በሚታይ ቦታ ላይ የሚለጥፈው ወይም በዜና ማሰራጫ የሚያስተላልፈው መግለጫ፡፡

ማስታወቂያ ኣወጣ በማስታወቂያ ገለፀ ወይም ነገረ፡፡

የማስታወቂያ ሰሌዳ ስ የተለያዩ ማስታወቂያዎች የሚለጠፉበት ሰሌዳ፡፡

ኣስተዋወቀ ግ 1.በፊት ትውውቅ ያልነበራቸውን ሰዎች አገናኘ፡ አነጋገረ፡፡ 2.ከዚህ በፊት ያልታየን ወይም ያልተሰማን እንግዳ ነገር እንዲታይ፥ እንዲሰማ ወይም እንዲታወቅ አደረገ፡፡

ኣስተዋዋቂ ቅ አንድን ጉዳይ በተመለከተ ለአድማጮች ወይም ለተመልካቾች የሚገልፅ ወይም የሚያስረዳ፡፡

ኣወን "ኣዎ"ን ተመ.

ኣወንታ "ኣዎ" ስር ተመ.

ኣወከ ግ በጠበጠ፡ ረበሸ፡ አስቸገረ፡፡

ሁከት (ሀውከት፥ እውከት) ስ ረብሻ፥ ብጥብጥ፡ ግርግር፡፡

ሁከተኛ (ሀውከተኛ፥ እውከተኛ) ቅ ረብሸኛ፡ በጥባጭ፡፡

ኣዋኪ ቅ በጥባጭ፡ ረባሽ፡ አስቸጋሪ፡፡

ታወከ ግ ተበጠበጠ፡ ተረበሸ፡ ተሸበረ፡ ተቸገረ፡፡

***ኣወከ**

ትውከት ስ ከተበላና ከተጠጣ በኋላ በህመም ወይም ባለመስማማት ከሆድ ተመልሶ በአፍ የሚወጣ ምግብና መጠጥ፡ ትፋት፡፡

ኣስታወከ ግ አስመለሰ፡ ለበቀ፡ ቋቅ አለ፡፡

ኣወደ^{1} ግ 1.ጥሩ ጥሩ ሸተተ፡፡ 2.ቤተክርስቲያንን አጠነ፡፡

ኣወደ^{2} ግ የቤተክርስቲያንን ዙሪያ ዞረ፡፡

ኡደት ስ 1.በክብረ በአል ቀን ታቦትን አጅቦ ቤተክርስቲያንን የመዞር ስነ ስርአት፡፡ 2.በድግግሞሽ የሚካሄድ የአንድ ድርጊት ክንዋኔ ወይም ሂደት፥ ዙረት፡፡

ታወደ ግ ታቦትን አጅቦ ቤተክርስቲያንን በመዞር የሚከናወነው ስነ ስርአት ተካሄደ ወይም ተፈፀመ፡፡

ኣሳወደ ግ ታቦት ሲነግስ በስነ ስርአቱ ላይ ተገኝቶ በአሉን አከበረ፡፡

ኣወደወደ ግ አውደለደለ፡ አደሸደሸ፡ አዘጠዘጠ፡፡

ኣወጀ ግ አዋጅ አወጣ ወይም ተናገረ፡፡

ኣዋጅ ስ በመንግስት የሚወጣና በይፋ የሚገለፅ ማናቸውም አቢይ ህግ፡ ደንብ፥ ውሳኔ፡፡

ኣዋጅ አወጣ/ነገረ አወጀ፡፡

ኣዋጅ ነጋሪ ስ ዘመናዊ የዜና ማሰራጫ ድርጅቶች ባልተስፋፉበት ወቅት በገበያ ቦታ ወይም በአደባባይ እየተገኘ መንግስት ያወጣውን አዋጅ ለህዝብ ያሰማ የነበረ ባለስልጣን ወይም የመንግስት ወኪል፡፡

ታወጀ ግ አዋጅ ወጣ ወይም ተነገረ፡፡

ኣሳወጀ ግ አንድን ጉዳይ (ውርስን፡...) በተመለከተ ያገባኛል የሚል ተቃዋሚ ወይም ተከራካሪ ካለ በተወሰነ ጊዜ እንዲቀርብ በጋዜጣ አሳወቀ፡፡

ኣው ስ የጅብ ጩሀት፡፡

ኣው አለ ግ ጮሀ (ጅብ)።

ኣውላ ስ ንቦች የሚያዘጋጁት የማር እንጀራ ውጥን ወይም ጅምር።

—**ኣዊ** "ዊ"ን ተመ.

ኣዋልድ ስ ቁጥራቸው ከሰማንያ አሃዱ መጻሕፍት ውስጥ ያልሆኑና እንደ ገድል፣ ድርሳን፣ ታምር የመሳሰሉ በሃይማኖት ሰዎች የተዘጋጁ መጻሕፍት።

ኣዋልድጌሳ ስ ፈካ ያለ ቡናማ መልክ ያለው፣ ጀርባው እንደደጋን የጎበጠ፣ አፉና አፍንጫው በረጅሙ ሞጥሟጣ ያሉ፣ ጆሮቹ ረጃጅም፣ ጅራቱ ከስሩ ደንደን ብሎ ከወደጫፉ ሾል ያለ፣ በቆላማ ስፍራዎች የሚኖርና በጣም ረጅም ምላስ ያለው ጉንዳንና ምስጥ የሚመገብ አሳማ የሚመስል የዱር እንስሳ(ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።

ኣዋራ "ኣቧራ"ን ተመ.

ኣዋሸ ቅ (ዘይ.) ትልቅ፣ ሰፊ። *ኣዋሽ በርሜል*።

ኣዋቂ "ኣወቀ" ስር ተመ.

ኣዋኪ "ኣወከ" ስር ተመ.

ኣዋዜ ስ 1. ከቅመም ጋር የተደቆሰና በጣም የታሸ በርበሬ ወይም ልቁጥ ድልህ። 2. ከሰናፍጭ ወይም በሶላ… ታሽቶ የሚዘጋጅ የበርበሬ ዱቄት ብጥብጥ ወይም ድልህ።

ኣዋጅ "ኣወጀ" ስር ተመ.

ኣውሊያ ስ ዛር።

ኣውላላ ቅ ግልጽና ሰፊ የሆነ (ስፍራ፣ ሜዳ…)።

ኣውላላ ሜዳ ስ ዛፍ፣ ቁጥቋጦ… የሌለበት ሰፊና የተንጣለለ ሜዳ።

ኣውሎ ንፋስ ስ በሰውም ሆነ በንብረት ላይ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ሃይለኛ ነፋስ።

ኣውራ ስ 1. ኮርማ፣ ወይፈን። 2. ያልተኮላሸና እንስትን ማጥቃት የሚችል ተባእት እንስሳ። 3. ዋና፣ አይነተኛ።

ኣውራ መንገድ ስ ሰፊ፣ ትልቅ መንገድ፣ ኣውራ ጎዳና።

ኣውራ ንብ ስ ንግስቲቱን ንብ የሚጠቃ ንብ።

ኣውራ ኣዘል ቅ ለመጠቃት የደረሰች (ጊደር)።

ኣውራ ዶሮ ስ ትልቅ ወንድ ዶሮ።

ኣውራ ዶሮ

ኣውራ ጎዳና ስ ኣውራ መንገድ።

ኣውራ ጣት ስ ከአመልካች ጣት ጎን የሚገኝ አጭርና ወፍራም ጣት(ስእሉን እጅ ስር ተመ.)።

የኣውራ እራት ስ ማር ሲቆረጥ ለንቡ ኣውራ ተብሎ የሚተው ትንሽ ማር።

ኣውራሪስ ስ ከጭንቅላቱ እስከ መሰሉ አፍንጫው ላይ አንድ ትልቅና አንድ ትንሽ ቀንድ ያሉት፣ ብዙውን ጊዜ ቆላማ በሆነ ስፍራ የሚኖርና የዛፍ ቅጠል፣ ቅርፊትና ስራስሮች የሚመገብ ቆዳሙና ሃይለኛ የዱር እንስሳ(ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።

ኣውራጅ "ወረደ" ስር ተመ.

ኣውሬ ስ 1. በዱር፣ በጫካ፣ በበረሃ የሚኖር እንደ አንበሳ፣ ጊንጥ፣ ጅብ፣ ኣያ፣ … ያለ ፍጥረት፣ ቅ 2. (ዘይ.) ክፉ፣ ጨካኝ፣ አረመኔ። 3. ከሰው የሚደበቅ ከሰው ርቆ ወይም ሸሽቶ ለብቻው የሚኖር።

ኣውሮፕላን "ኣይሮፕላን"ን ተመ.

የኣውሬ እራት ሆነ በአውሬ ተበላ።

ኣውታር "*ወተረ" ስር ተመ.

ኣውታንቲ ስ እንደ ጭነት መኪና፣ ኣውቶቡስ፣… ባሉ የንግድ መኪናዎች ውስጥ ቴክኒክ ነክ የሆነ ወይም ያልሆነ አገልግሎት የሚሰጥ የሾፌር ረዳት።

ኣውቶማቲክ ስ 1. በውስጣዊ ባህርዩ ምክንያት በራሱ ሃይል በመንቀሳቀስ የተወሰነ ተግባር የማከናወን ችሎታ ያለው መሳሪያ። 2. (ዘይ.) ፈጣን፣ ቀልጣፋ። *እገሌ ሲሰራ ኣውቶማቲክ ነው*።

ኣውቶሞቢል ስ ለሰው መጓጓዣ የሚያገለግል አነስተኛ መኪና፣ የቤት መኪና።

ኣውቶቡስ ስ ከክፍለ ሃገር ወደ ክፍለ ሃገር ወይም በከተማ ውስጥ በአንድ ጊዜ ብዙ ሰዎችን ማጓጓዝ የሚችል ትልቅ መኪና።

ኣውቶቡስ ማቆሚያ ስ የከተማ ኣውቶቡስ በተወሰነ ርቀት እየቆመ ሰዎችን የሚያሳፍርበትና የሚያወርድበት ቦታ፣ ፌርማታ።

ኣውዝ (ሃውዝ) ስ የተቀቀለ የሎሚ ውሃ።

ኣውድ ስ አደባባይ፣ ሸንጎ፣ የህዝብ መሰብሰቢያ።

ኣውደ ኣመት ስ የዘመን መለወጫ በአል ወይም በየአመቱ የሚከበር እንደ ገና፣ ፋሲካ ያለ ኣቢይ በአል።

ኣውድማ (ውድማ) ስ እህል የሚወቃበት የተስተካከለና የለሰለሰ ቦታ።

ኣውጥ ስ ከፈፍ ባለ ለስላሳ ሽፋን ውስጥ የሚገኝና ሲበስል ሊበላ የሚችል ፍሬ ያለው የተክል አይነት። ፍሬውም ኣውጥ ይባላል።

ኣዎ (ኣወን፥ ኣዎን) ግ አንድን ነገር ወይም ድርጊት ልክ ነው፡ እውነት ነው ወይም ነው ለማለት የሚያገለግል ቃል። *ድሙት ጥርስ ኣላት? ኣዎን ኣላት*።

ኣወንታ ስ እሺታ፡ ይሁንታ።

ኣዘለ ግ 1.በጀርባ ተሸከመ (ልጅን ወይም ሌላን)። 2. በጎን ፍራ ያዘ፡ ሸጎጠ (በቃሉ)። 3. ያዘ፡ አካተተ። *ቁም ነገር የኣዘለ ንግግር*።

ኣዛዩን ነካሽ በችግር ጊዜ በደረሰለት ወይም ውለታ በዋለለት ሰው ላይ ተንኮል የሚፈፅም ሰው።

ማዘያ ስ 1.ልጅን በጀርባ መሸከሚያ ጨርቅ፡ አንቀልባ። 2.እቃን በጀርባ ለመያዝ ወይም ለመሸከም የሚያስችል ጨርቅ።

—ኣዘል ቅ —የያዘ፡—የካተተ። *ቁም ነገር ኣዘል*።

እዝል ስ 1.ሸክም። 2.ተጨማሪ ወይም አባሪ የሆነ ነገር (ፅሁፍ፡ መረጃ፡ ...)።

ታዘለ ግ 1.በጀርባ ተያዘ። 2.እራሱን መቻል አቅቶው፡ የሌላ ሰው ሸክም ወይም ጥገኛ ሆነ።

ተዛዘለ ግ 1.አንዱ በአንዱ ላይ ሆነ፡ ተነባበረ፡ ተደራረበ። 2.አንዱ ሌላውን በጀርባው ተሸከመ።

ኣስተዛዘለ ግ 1.አንዱን በአንዱ ላይ አደረገ፡ አነባበረ፡ አደራረበ። 2.አንዱ ሌላውን እንዲሸከም አደረገ።

ኣዘመረ^{1} ግ 1.እንደ ማረስና መዝራት ያለ የእርሻ ስራ ሰራ። 2.አመረተ።

ኣዝመራ ስ ሰብል፡ የእርሻ ውጤት።

ኣዝመራው ሰጥቷል ብዙ ሰብል ወይም ምርት ተገኝቷል።

ኣዘመረ^{2} **"ዘመረ"** ስር ተመ.

ኣዘረጠ ግ 1.በሃይል መታ፡ ደበደበ። *በዱላ ኣዘረጠው*። 2.ጨፈጨፈ፡ ሞሸለቀ፡ አዋረደ። *በስድብ ኣዘረጠው*።

ኣዘራ^{1} ግ ክፉኛ መታ ወይም ሰደበ።

ኣዘራ^{2} **"ዘራ"** ስር ተመ.

ኣዘቅት ስ ጥልቅ ጉድጓድ።

ኣዘበዘበ ግ 1.ተንጠለጠለ፡ ለመፍረስ ወይም ለመውደቅ ተቃረበ (ያረጀ ካብ፥ የግድግዳ ምርጊት)። 2.ያለ ቅጥ ወፈረ (ከምቾት የተነሳ)።

ኣዘቦት [ቀን] ስ በአል ያልሆነ ተራ የስራ ቀን።

ኣዘነ ግ 1.ተፀፀተ፥ ተከፋ፡ ተቆረቆረ፡ ተከዘ። 2.ራራ።

ኣዘኔታ (ሃዘኔታ) ስ ደግነት፥ ርህራሄ።

ኣዘን "ሃዘን"ን ተመ.

ኣዛኝ ቅ ደግ፥ ሩህሩህ።

ኣዛኝ ቅቤ ኣንጓች ተቆርቋሪ መሳይ፥ አልኩ ባይ።

ኣዛኝቱ ቅ የድንግል ማሪያም የቅፅል ስም።

[የ]እዝን ስ ሃዘን ወይም ለቅሶ ቤት የሚወሰድ ምግብ፥ መጠጥ፥...።

ተዛዘነ ግ ተሳሰበ፡ ተረዳዳ፥ አንተ ትብስ አንተ ትብስ ተባባለ።

ኣሳዘነ ግ 1.አስከፋ፡ አስቀየመ፥ ቅር አሰኘ። 2.አራራ፡ አባባ።

ኣስተዛዘነ ግ ዘመድ ወይም ወዳጅ የሞተበትን ሰው አዋየ፡ አፅናና፥ አረጋጋ።

ማስተዛዘኛ ስ 1.የእዝን። 2.የተገዛበትን ዋጋ ብቻ ሊያስገኝ የሚችል የሎተሪ እጣ።

ኣዘዘ ግ አንድ ነገር እንዲሰራ ትዕዛዝ ሰጠ።

ኣዘዘበት ፈረደበት፡ መጥፎ እድል ወይም መጥፎ አጋጣሚ አገኘው።

ማዘዣ ስ 1.አንድ ነገር እንዲደረግ ወይም እንዲከበር የተፃፈ ትእዛዝ፥ ደብዳቤ። 2.ከላይ በኩል አድራሻና አርማ ያለውና ልዩ ልዩ ጉዳዮች የሚፃፉበት የመንግስት ወይም የግል መስሪያ ቤት ወረቀት።

ኣዛዥ ስ 1.የቤተ መንግስት ወይም የታላላቅ መኳንንት የንብረት ሹም ወይም አስተዳዳሪ። 2.የበላይ ሃላፊ፥ አለቃ። *የጦር ሃይሎች ኣዛዥ*።

እዝ ስ በአንድ ማእከል ስር አመራርን የሚቀበል ምድብ፡ ቀጣና፥ ...።

[የ] እዝ ኢኮኖሚ ስ በኢኮኖሚው ዘርፍ ከግል ባለሃብቶች ተሳትፎ ይልቅ መንግስት ኢኮኖሚውን በብቸኝነት የሚቆጣጠርበት ሁኔታ።

ታዘዘ ግ 1. እሺ አለ፡ ትእዛዝ ተቀበለ። 2.አንድ ስራ በተወሰነ ጊዜ እንዲሰራ ተነገረ፥ ትእዛዝ ተሰጠ። 3.ከተጠቃሚው ወይም ከተገልጋዩ ትእዛዝ ተቀበለ ወይም የሚፈልጉትን ነገር ጠየቀ፡ አስተናገደ (ቡና ቤት፥ ምግብ ቤት፥...)።

ታዛዥ ቅ 1.ትሁት፥ ሰው አክባሪ፥ እሺ ባይ። 2.አሽከር፥ አገልጋይ፥ ሎሌ።

ትእዛዝ ስ 1.አንድ ነገር መሰራት ያለበት መሆኑን የሚገልፅ የበላይ ውሳኔ። 2.ፍርጃ፥ ድንገተኛ አደጋ።

ትእዛዝ አንቀፅ አንድ ነገር መደረግ ወይም መከናወን ያለበት መሆኑን ለመግለፅ የሚነገር ግስ (ለምሳሌ ሂድ፥ እንድትሄድ)።

ኣዘገበ ግ አለመ፡ አነጣጠረ።

ኣዙሪት "ዞረ" ስር ተመ.

ኣዚም ስ የሚያፈዝ ወይም የሚያደነዝዝ መተት፥ አስማት።

አዚመኛ ቅ የሚያፈዝ ወይም የሚያደነግዝ መተት ወይም አስማት በሰው ላይ የሚያደርግ።

አዚማም ቅ. 1.አዚም የተደረገበት (በሰው፣ ነገር)። 2.የሚቀፍ፣ የሚከብድ።

አዚፋ ስ የተቀቀለ ምስር ከተደቆሰ በኋላ ከቃሪያ፣ ከሽንኩርት፣... ጋር ተዋህዶና ተደባልቆ የሚሰራ የፆም ምግብ አይነት።

አዛመ ቅ አንቀጠቀጠ፣ አንዘፈዘፈ (ውሃ፣ ብርድ፣...)።

አዛመረ ግ አወላዳ፣ አሳወሰ፣ አስናዘረ።

አያዛምርም አያስናዝርም፣ አያወላዳም።

አዛምር ስ የእፅዋት አይነት።

አዛቆን^{1} ግ አደቆነ።

አዛቆን^{2} "ዛቆነ" ስር ተመ.

አዛባ ስ 1.የላቀጠ የከብቶች እበት። 2.ዘይ፣ (ስድብ) ሬሁ፣ ሰነፍ፣ ገልቱ።

አዛኝ "አዘነ" ስር ተመ.

አዛኝቱ ዝ.ክ.

አዛውንት ስ ሽማግሌ ወይም አሮጊት።

አዛዥ "አዘዘ" ስር ተመ.

አዛጋ ግ አፋሸገ፣ አፉን አላቀቀ።

አዜብ ስ በደቡብና በምስራቅ መካከል ያለ የአለም ማእዘን አቅጣጫ (በተጨማሪ ማእዘን ስር ተመ.)።

አዝመራ "አዘመረ^{2}" ስር ተመ.

አዝማሚያ "ዘመመ^{1}" ስር ተመ.

አዝራር ስ ከተለያየ ነገር (ከቀንድ፣ ከእንጨት፣...) በተለያየ ቅርፅ የሚሰራ የልብስ ቁልፍ።

አዞ ስ በደረት ከሚሳቡት አራዊት ሁሉ የመጨረሻው ትልቅ የሆነ፣ ርዝመቱ እስከ 6 ሜትር የሚደርስ፣ አካሉ ከወደላይ ደንዳና ሆኖ እንደ ጥፍር በጠነከረ ቅርፊት የተሸፈነ፣ ከወደሆዱ ቆዳው ለስላሳ የሆነ፣ መንጋጋ ጥርሶችና ረጅም አፍ ያለው፣ በብዛት በሞቃት አካባቢ በሚገኙ ትልልቅ ጅረቶችና ሃይቆች ውስጥ የሚኖር የውሃ ውስጥ አውሬ።

አዞ ሃረግ ስ ቅጠሉ ሰውነትን ሊያቃጥልና ሊያቆስል የሚችልና እንደ ልጥ ለማሰሪያ ወይም ለቀፎ መስሪያ፣... የሚያገለግል ጠንካራና ረጅም የሆነ የሃረግ አይነት።

አዞጠ ግ በሃይል መታ፣ ገረፈ፣ ደበደበ።

አገ ግ 1.አመረቀዘ፣ መግል። 2.በትንሹ ማፍሰስ ጀመረ። *እንስራው አገ።*

አየ ግ 1.ተመለከተ፣ አተኮረ፣ ተረዳ፣ መረመረ፣ አስተዋለ። 2.ጎበኘ፣ ጠየቀ። 3.ታዘበ።

አየሁህ 1.ታዘብኩህ። 2.ልጆች የሚጫወቱት የድብብቆሽ ጨዋታ አይነት።

አላየሁም 1. አላጋጠመኝም፣ አላገኘሁም። *እንደ እሱ ያለ ሰው አላየሁም።* 2.አልወሰድኩም፣ አልነካሁም። *የእሱን ገንዘብ አላየሁም።*

እዩኝ ባይ 1.በሚያገባው ቦታ ወይም ነገር ውስጥ ጥልቅ የሚል። 2.ያልሆነውን መስሎ መታየት የሚሻ።

ታየ ግ ታወቀ፣ ተገለፀ፣ ተከሰተ።

ታይቶ ጠፋ ሞተ፣ ተቀጨ።

ታየበት ተፈረደበት።

ታየው 1.ተረዳው፣ ተገነዘበው። 2.ተገለፀለት።

መታያ (መተያያ) ስ ገፀበረከት፣ ስጦታ፣ እጅ መንሻ።

ተያየ ግ በአካል ተገናኘ።

ትይዩ ስ ፊት ለፊት፣ ግድ ለግድ።

አሳየ ግ 1.አመለከተ፣ ጠቆመ፣ መራ። 2.አስረዳ፣ አሳወቀ። 3 አቀመሰ (በዱላ፣ በስድብ፣...)።

አሳይቶ መለሰው በጠና ታሞ ዳነ ወይም ከከባድ አደጋ ተረፈ።

ያሳየኝ 1.እግዚአብሄር ይፍረደኝ። 2.(ለማማት) ችግር፣ ስቃይ ገጥሞት ለማየት ያብቃኝ። *የእርሱን ነገር ያሳየኝ።*

አስተያየ ግ 1.አመሳከረ፣ አገናዘበ። 2.አወዳደረ፣ አነፃፀረ።

አስተያየት ስ 1.አመለካከት። 2.ሃሳብ። *ጥሩ አስተያየት ሰጠኝ።*

አስተያየት አደረገ 1.ዋጋ ቀነሰ። *እቃውን አስተያየት አድርጎ ሸጠልኝ።* 2.ራራ፣ አዘነ። *ለእስረኞቹ አስተያየት አደረገላቸው።*

አየለ ግ በረታ፣ ጠነከረ፣ ጠና።

ሃይል በፊደል ተራው ተመ.

ሃይለቃል "ሃይል" ስር ተመ.

ሃያል ዝ.ክ.

አየመ ግ በድጋሚ አረሰ፣ አለሰለሰ (ማሳን)።

አየር ስ 1.መሬትን የከበበና ህይወት ላላቸው ነገሮች አስፈላጊ የሆነ የብዙ ጋዞች ጥርቅም። 2.ከምድር በላይ ከጠፈር በታች ያለ ቦታ። 3.አይሮፕላን።

አየር ለወጠ ከነበረበት ቦታ ወደ ሌላ ሄደ (ለእረፍት ወይም በጤና ምክንያት)።

አየር ማረፊያ ስ የአይሮፕላን ማረፊያ።

አየር ተቀበለ "ነፋስ" ስር "ነፋስ

ተቀበለ"ን ተመ.

አየር ወሰደ 1.አየር ወደ ሳምባው አስገባ፡ ወደ ውስጥ ተነፈሰ።2.አየር ተቀበለ።

አየር ሃይል ስ 1.በተዋጊ አይሮፕላኖች የአየር ላይ ውጊያ ማስልጠኛ ተቋም። 2.በዚሁ ተቋም የሰለጠነ ወታደር።

አየር መቃወሚያ ስ የጠላትን ተዋጊ አውሮፕላን መትቶ ለመጣል የሚያገለግል የጦር መሳሪያ።

አየር መንገድ ስ ሰውን ወይም እቃን በአየር የሚያጓጉዝ የንግድ ድርጅት።

አየር ትራንስፖርት ስ በአየር ላይ የሚደረግ ጉዞን በበላይነት የሚቆጣጠር የበላይ ሃላፊ ወይም ተጠሪ የሆነ መስሪያ ቤት።

አየር ወለድ ስ 1.ከአውሮፕላን ላይ በፓራሹት እየወረዱ የሚዋጉ ወታደሮች የሚሰለጥኑበት ተቋም። 2. በዚሁ ተቋም የሰለጠነ ወታደር።

የአየር መልእክት ስ በአውሮፕላን የሚላክ መልእክት ወይም ደብዳቤ።

የአየር ጠባይ ስ አንድ የተወሰነ ቦታ በተወሰነ ጊዜ የሚኖረው የዝናም፡ የነፋስ፡ የሙቀት፡... ሁኔታ።

አያ (አይያ፥ አይዋ) ስ ታናሽ ታላቅ ወንድሙን ወይም ዘመዱን ለመጥራት የሚጠቀምበት የአክብሮት መጥሪያ ወይም ስምን ተከትሎ እየገባ የባእታይ ያታን በአክብሮት ለመጥራት የሚያገለግል ቃል። *አያ ከበደ*፡

አያሌ (አያል) ቅ ብዙ፡ በርካታ።

አያት ስ የአባት ወይም የእናት አባት ወይም እናት።

አያያዘ "ያዘ" ስር ተመ.

አዬ (ቃ.አ.) ትራታን፡ ጥርጣሬን፡... ለመግለፅ የሚነገር ቃል።

አዬ ጉድ ቃ.አ. ማዘንን፡ መገረምን፡ መደነቅን፡... ለመግለፅ የሚነገር ቃል። *አዬ ጉድ! ጨክነህ ከአገር ልትወጣ ነው?*

አይ 1.አይደለም ወይም አይሆንም ለማለት የሚያገለግል አፍራሽ ቃል። 2.ቁጣን ለመግለፅ የማነገር ቃል። *አይ! እንግዲህ አትጨሁብኝ*፡

አይሁድ ስ (ዘይ.) እርጉም፡ ክፉ፡ ከሃዲ።

አይሮፕላን(አውሮፕላን) ስ ሰውንና እቃን በሰማይ ላይ ለማጓጓዝ የሚችል ሰው ሰራሽ በራሪ አካል፡ አየር።

አይሮፕላን ማረፊያ ስ አይሮፕላን የሚያርፍበት ቦታ ወይም ጣቢያ፡ አየር ማረፊያ።

አይበሉባ (አይበሉብሽ) ስ የእጅ መዳፍና ጣት ጀርባ የሆነው የሰውነት ክፍል(በእሉን እጅ ስር ተመ.)።

አይበሉብሽ ጥፌ ስ በጣት ጀርባ የሚመታ ጥፊ ፡ ቃሪያ ጥፊ።

አይቡት ስ ከወይፈን ቆዳ የሚሰራ ስልቻ።

አይብ ስ ቅቤው የወጣለት ወተት (ወንጫት) ከተፈላ በኋላ ዘቅጦ ከአጓት ስር የሚቀረው የምግብ አይነት።

አይት ስ የባል እህት ወይም የወንድም ሚስት።

አይነምድር ስ ሰገራ፡ አር።

አይነት^{1} ስ 1.ቀለምን፡ መልክን፡ ጠባይን፡ ተፈጥሮን፡ ሁኔታን፡ ... ለመግለፅ ወይም ለመጠየቅ የሚያገለግል ቃል። *ልብስ ይሉሃል የዚህ አይነት ነው፡ምን አይነት ሰው ነው ፈልጎኝ የነበር?* 2.ቁጥራቸው ከአንድ በላይ የሆኑ ልዩ ልዩ ምግቦች።

የአይነት ለውጥ ስ (ፍል.) በአንድ ነገር ላይ (ቀድሞ በነበረው ጠቅላላ ባህርይ፡ መልክ፡ ምንነት ላይ) ፈጣን በሆነ መንገድ ወይም በቅፅበት የሚመጣ መሰረታዊ ለውጥ።

አይነተኛ ቅ ዋነኛ፡ አቢይ።

አይነት^{2} ስ እከክ የሚመስል ቁስል።

አይን ስ 1.የማያ ወይም የመመልከቻ አካል። 2.በእንጀራ፡ በማር ከዳ፡... ላይ አይን መስሎ የሚታይ ጠቃጠቆ። 3.ብስ፡ ቀዳዳ (የመርፌ፡ የመዋጥ፥...)። 4.በእንጨት ግንድ ላይ ቅርንጫፍ ከመውጣቱ በፊት የምትወጣ ጉጥ። 5.በእጅ ባትሪ ወይም በተሽከርካሪዎች መብራት ውስጥ የምትገኝ ትንሽ አምፑል።



አይን፡ና ፍቺ

ለአይን አይሞላም በጣም ትንሽ ወይም ጥቂት ነው።

ለአይን ያዘ ጨለም አለ።

በአይን ሲጋ በአካል፥ ፊት ለፊት። *በአይን ሲጋ ለመገናኘት ያብቃን*፡

በአይን ቁራኛ በስውር ክትትል። *ሌባዉ በአይንቁራኛ እየተጠበቀ ነው።*

በአይኑ ላይ ዞረ/ሄደ 1.ናፈቀ፥ ትዝታው መጣበት። 2.አማረ፡ አሰኘ።

በአይኔ መጣህ በጣም የምወደውንና

እንዲነካብኝ የማልፈልገውን ነገር ነካህ፡ ጠየቅህ፣ አነሳህ፡ ...።

አይኑ ላይ ጣለበት አይኑ ብሬት ላይ ነጭ ነገር በመውጣት የማየት ሃይሉን በመጠኑ ጋረደው።

አይኑ ሰከረ የሚያየው ነገር ከመብዛቱ የተነሳ የሚመርጠውን አጣ።

አይኑ ቀላ /ደም ለበሰ ተመቀኘ፥ ቀና።

አይኑ በራ እውር የነበረው አይኑ ዳነ።

አይኑ ባከነ አይኑ አንድ ነገር ለማየት ተንከራተተ፡ ተቅበዘበዘ፡ ወዲያና ወዲህ አየ።

አይኑ ብር አለ 1. ከህመም፡ ከድካም፥... የተነሳ አይኑ ፈዘዘ። 2.ናፈቀ፥ ለማየት ጓጓ።

አይኑ ተመረገ አይኑ አልገለጥ አለ፡ ተደፈነ።

አይኑ ተንከራተተ አንድን ነገር ለማግኘት ጎምጅቶ ወይም ጓጉቶ ወዲያ ወዲህ ተመለከተ።

አይኑ ተከፈተ/ተገለጠ ማስተዋልና ማመዛዘን ቻለ፡ ክፉና ደጉን ወይም ጠቃሚና ጎጂውን ለየ፣ ብልህ ሆነ።

አይኑ አረፈበት/ወደቀበት ወደደው፡ አይኑን ጣለበት።

አይኑ እንባ አቀረረ እንባው በአይኑ ሞላ።

አይኑ ደም ጎረሰ 1.ተበሳጨ፡ ተናደደ። 2.ተመቀኘ፡ ቀና።

አይኑ ደገደገ አይኑ ፈዘዘ ወይም ደከመ (በእድሜ መግፋት)።

አይኑ ደፈረሰ 1.አይኑ ቀላ፤ ደም መሰለ። 2.ተቆጣ። ተመቀኘ፥ ቀና።

አይኑ ጠገበ የሚፈልገውን ነገር በብዛት በማግኘቱ በማየት ብቻ ረካ ወይም ጠገበ።

አይኑ ፈሰሰ አይኑ ፈረጠ፥ ጠፋ፡ ታወረ።

አይኑ ፈጠጠ 1.ተጨነቀ። 2.ክው አለ፡ ደነገጠ።

አይኑን ሰበረ ከማፈር፥ ከመሽኮርመም የተነሳ ወደ መሬት ተመለከተ።

አይኑን ሰካ/ተከለ 1.ወደ አንድ አቅጣጫ ብቻ ተመለከተ ((በህመም ምክንያት))። 2.አተኩሮ ተመለከተ፥ ትክ ብሎ አየ።

አይኑን ቁልጭ አደረገ 1.አይኑን ገለጠ፥ ተመለከተ። 2.ከእንቅልፉ ነቃ።

አይኑን ቁልጭ ቁልጭ አደረገ 1.ጓጓ፥ በጉጉት አየ። 2.ከመደንገጥ፥ ከመገረም፥... የተነሳ ሁኔታዎችን በአርምሞ ተመለከተ።

አይኑን በአይኑ አየ ልጅ ወለደ።

አይኑን በጨው አጥቦ እፍረቱን፡ ደሉኝታውን ትቶ።

አይኑን አያሳየኝ አለ ጠላው፥ አራቀው።

አይኑን አጎረጠ/ጎለጎለ አይኑን አፈጠጠ፡ አጉረጠረጠ።

አይኑን ከደነ 1.አይኑን ጨፈነ። 2.እንቅልፍ ያዘው፥ አሸለበው።

አይኑን ወረወረ አሻግሮ አየ።

አይኑን ገለጠ 1.ፊደል ቆጠረ፥ ተማረ። 2.ነቃ፡ አወቀ።

አይኑን ጋረደው /ከለለው ማየት ተሳነው።

አይኑን ጣለበት ወደደው፥ ፈለገው፥ መረጠው።

አይኔን ግንባር ያድርገው አለ አላየሁም፡ አልሰማሁም፡ አላውቅም አለ።

አይን ለአይን ተያየ ከተለየው ወይም ከናፈቀው ሰው ጋር ተገናኘ፥ ለመተያየት በቃ።

አይን ለአይን ተጋጩ አንዱ ሌላውን በስርቆት ለማየት ሲል ወይም ባጋጣሚ ሁለቱም ተያዩ።

አይን በላው 1.ቡዳ በላው። 2.ተስፋ ተጥሎበት ባለ እንደተጠበቀው ሳይሆን ቀረ፥ ተበላሸ።

አይን በአይን በገሃድ ወይም በግልፅ።

አይን ነው ዋና፥ አይነተኛ፥ ብቃት ያለው ነው። *ሰውየው ለተመደበበት ስራ አይን ነው።*

አይን አወጣ ከመጠን በላይ ደፈረ፥ እፍረተ ቢስ ሆነ።

አይን አውጣ ቅ የማያፍር፥ ደሉኝታ ቢስ።

አይን አዋጅ ሆነበት ሁሉም ስለአማረው ምርጫውን ለመወሰን ተቸገረ።

አይን ገባ 1.ቡዳ በላው። 2.ሁሉም አተኮረበት፥ የሁሉንም ስሜት ሳበ።

አይንህን ለአፈር አለ ፈፅሞ ጠላ።

አይንና ናጫ / አፈር የማይስማማ፥ የማይጣጣም።

አይነ ሌባ ቅ የአመንዝራነት ጠባይ ያለው፥ አይኑ የሚቃብዝ፣ በአይኑ የሚጠቅስ።

አይነ ማዝ ስ ትራኮማ የሚባል የአይን በሽታ።

አይነ ስብ ስ 1. ከአይን በታች በኩል ያለ ስስ ቆዳ። 2.የአይን ጉድጓድ።

አይነ ስውር ስ አይኑ ለማየት የማይችል፡ እውር።

አይነ ቀላዋጭ ቅ ሁሉንም ለማየት አይኑ የሚራወጥ፡ የሚቃበዝ።

አይነ ቆሎ ቅ አይነ ትልልቅ።

አይን በላ ቅ (ስድብ) እፍረተ ቢስ፡ አይን አውጣ።

አይነ በጎ ስ ከጨጓራ ጋር ተያይዞ የሚገኝ የማር እንጀራ የመሰለ አይን ያለው ከእንስሳት የሆድ እቃ አንዱ።

አይን አፋር ስ እንግዳ ሰውን ትክ ብሎ ማየት ወይም ማነጋገር የሚፈራና የሚያፍር ሰው።

የአይን መቃድ ስ የአይን የቅዱ ቅርፅ።

የአይን ማሚቶ ስ የአይን ብሌን።

የአይን ምስክር ስ አንድ ድርጊት ሲፈፀም በቦታው የነበረና የተመለከተ እማኝ።

የአይን ቆብ ስ ከቅንድብ ቢታች ያለው የአይን መከደኛ፡ ሽፋን (ስእሉን አይን ስር ተመ.)።

የአይን ብረት/ብሌን ስ ጥቁሩ የአይን ክፍል።

የአይን አባት ስ ህፃን ወንድ ሲገረዝ አይኑን የሚይዝለትና በዚህም የተነሳ ዘመድ የሚሆን ሰው።

የአይን እናት ህፃን ሴት ስትገረዝ አይኗን የምትይዝላትና በዚህም የተነሳ ዘመድ የምትሆን ሴት።

አይናማ ቅ ጎላ ጎላ ያለ አይን ያለው፤ አይነ ትልልቅ።

አይናማ ድንጋይ ስ እንደ ብስ ያለ ጠቃጠቆ ያለበት ድንጋይ።

አይዋ "አያ"ን ተመ.

አይያ ዝ.ከ.

አይደለም የ"ነው" ተቃራኒ።

አይደርቄ "ደረቀ" ስር ተመ.

አይጥ^{1} ስ በቤት አካባቢ ወይም በዱር የሚኖርና በሰብልም ሆነ በቤት ውስጥ የተለያዩ ምግቦችንና ነገሮችን በመብላት ጥፋት የሚያደርስ ጅራተ ረጅም ትንሽ አውሬ።

አይጠ መጎጥ ስ አፉ ሾል ያለና የአይጥ መልክ ያለው አነስተኛ አውሬ።

[የ]አይጥ ሃረግ ስ የተንዠረገገ ድቡልቡል ፍሬ ያለው ቀጭን ሃረግ፤ እንሰሳት።

[የ]አይጥ ምስር ስ ፍሬው ምስር የሚመስል የእፅዋት አይነት።

[የ]አይጥ አተር ስ እንደ አተር ያለ ፍሬና ሃረግ ያለው የእፅዋት አይነት።

አይጥ^{2} ስ የክንድ ጡንቻ።

አደለ ግ ሰጠ፤ አከፋፈለ።

ማደያ ስ ማከፋፈያ።

አዳይ ቅ 1.አሳሳፊ፡ አስተናባሪ።2.አከፋፋይ።

እደላ ስ የማዳረስ፡ የማከፋፈል ስራ፤ ስርጭት።

እድል ስ 1.እጣ ክፍል፤ ግንባር። 2.ድርሻ።

እድሉ ተሰበረ እድሉ ተሰናከለ፡ ኑሮ ሳይሳካለት ቀረ።

እድለ ሰባራ ቅ እድለ ቢስ፡ ያልታደለ፤ መልካም ወይም ጥሩ ነገር የማይገጥመው።

እድሉ ተዘጋ 1.በእድሉ እንዳይጠቀምበት ሆነ። 2. በነበረው እድል መጠቀም ተከለከለ፤ ታገደ።

እድሉ ጠባብ ነው የነገሩ የመሆን ወይም የመፈፀም ተስፋው ያነሰ ነው።

እድለ ቢስ ቅ መልካም ነገር የማይገጥመው፤ ያልታደለ።

እድል ፈንታ ስ እጣ ፋንታ፤ ድርሻ።

እድለኛ ቅ መልካም ወይም ጥሩ ነገር የገጠመው ወይም የሚገጥመው።

እድላም ዝ.ከ.

ታደለ ግ ጥሩ ነገር አገኘ፡ መልካም እድል ገጠመው።

የታደለ ቅ እድለኛ።

አደመ^{1} ግ አሴረ፤ ዶለተ።

አድማ ስ ሴራ፤ ዱለታ።

አድማ መታ አሴረ።

አድመኛ ቅ ለተንኮል ስራ ሊሎችን የሚያስተባብር፤ ሴረኛ።

አሳደመ ግ ለተንኮል ስራ ሊሎችን አስተባበረ፤ ሴራ ቀረጠ ወይም አድማ መታ።

አደመ^{2} ግ ጠራ፤ ጋበዘ (ለሰርግ፡ ለግብዣ ፤...)።

እድምተኛ(እድመኛ) ስ ለሰርግ ወይም ለግብዣ፤... የተጠራ ሰው፡ ተጋባዥ።

ታደመ ግ ተጠራ፤ ተጋበዘ (ለሰርግ፡ ለግብዣ)።

ታዳሚ ስ ተጋባዥ፤ ተጠሪ።

አደረ ግ 1.በቤት ውስጥ ወይም ሌላ ስፍራ ሆኖ ሌሊቱን አሳለፈ ወይም አነጋ። 2.(ዘይ.) ተስማምቶና መስሎ ኖረ። *ከነሱ ማደር ይቻላል።* 3. ለሌላ ጊዜ ተላለፈ። *ውሳኔው በእለቱ ሳይሰጥ አደረ።*

—አደረበት ያዘው። *ቅናት አደረበት/በሽታ አደረበት።*

አድሮ ልጅ ከርሞ ጥጃ፤ እድገት ወይም መሻሻል የማያሳይ።

እያደር ተው.ግ ቀስ በቀስ፡ እየሰነበተ፤

እየቆየ።

ማደሪያ ስ 1.ሌሊቱን ማሳለፊያ፥ መኝታ ቦታ ወይም ቤት። 2.መተዳደሪያ (ስራ፥...)።

አዳሪ ቅ 1.የሌሊት ተረኛ (የተወሰነ ተግባር ለማከናወን)። 2.በሚማርበት ቦታ የሚኖር (ተማሪ ወይም ሰልጣኝ)።

አዳሪ ትምህርት ቤት ስ ተማሪዎች የምግብ፥ የመኝታ፥... አገልግሎት እያገኙ የሚማሩበት ት/ቤት።

አዳር ስ 1.ትዳር። 2-ኑሮ። 3.የአንድ ሌሊት ጊዜ። 4.ማደሪያ።

አዳሩ ሞቀ ትዳሩ ሰመረ፥ ሃብት ንብረት አገኘ።

አዳሩን ሄደ ወይም መጣ ለማደር ሄደ ወይም መጣ።

አድርባይ ቅ ለጥቅሙ ሲል የሚያጎበድድ፥ ተለማማጭ።

ተዳደረ ግ 1. በተወሰነ ደንብ ተመራ 2. ተኳኋነ፥ ተስማማ፥ ተመሳሰሉ ኖረ። 2.ኖረ። *በእርሻ ስራ ነው የሚተዳደረው።*

መተዳደሪያ ስ 1.ስራ። 2.ደንብ፤ ስርአት።

ተዳደረ ቅ ከሌላው ጋር ተስማምቶ መኖር የሚችል።

መስተዳድር ስ የአንድን ሃገር የፖለቲካ፥ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ጉዳዮችን በሃላፊነት የሚመራ ከፍተኛው የመንግስት ስልጣን አካል።

አሳደረ ግ 1. በሃላፊነት ያዘ፤ ተንከባከበ (ቤተሰብን)። 2.ለሌላ ጊዜ አስተላለፈ (ጉዳይን፥ስራን፥...)።

አሳዳሪ ስ 1. የቤተሰብ ሃላፊ፥ ተንከባካቢ። *አሳዳሪሽ ማነው?* 2.በቤት ሙሽራ ቤት የወንድን ሙሽራ ተቀብሎ የሚያስተናግድና የሚጋብዝ ሰው። 3.የአሽከር፥ የሎሌ፥ የገረድ ጌታ።

አስተዳደረ ግ 1.ተቆጣጠረ፥ መራ፥ አኖረ (ህዝብን፥ ቤተሰብን፥ ሰራተኛን)። 2.አብሮ አደረ።

አስተዳደር ስ 1.የስራ አመራርና የሃላፊነት ተግባር። 2.የሰው ሃይልንና የስራን አመራር በተመለከተ ስልጣንና ሃላፊነት ያለው አካል። 3.የሌሊቱ አጠቃላይ ሁኔታ ወይም አኳሃን። *የዛሬ ሌሊት አስተዳደርህ እንዴት ነበር? አልተኛህም?* 4.የቤተሰብ አኗኗር ሁኔታ።

አስተዳዳሪ ስ መሪ፥ ሃላፊ (የድርጅት፥ የተወሰነ ሃገር ክፍል፥...)።ቅ 2.አብሮ የሚያድር።

አደራ እንደ አደርጉልኝ፥ ጠብቁልኝ፥ አስቀምጡልኝ፥... የመሳሰሉት ቃላት የሚያስተላልፉትን መልእክት በተመለከተ የሚነገር የጠበቀ ተማፅኖ፥ ልመና፥ማሳሰቢያ፥... ቃል። *አደራ ይህንን እቃ አስቀምጥልኝ /አደራ ነገ እንድትመጣ።*

ባለአደራ አንድን ነገር ለማከናወን፥ ለማስቀመጥ፥... በፈቃደኝነት ሃላፊነትን የተቀበለ ሰው።

አደራ በላ ግ 1.አስቀምጥልኝ፥ ያዝልኝ፥... የተባለውን እቃ ወይም ገንዘብ፥... አጠፋ፥ ተጠቀመበት። ቅ 2.እንዲጠብቅ፥ እንዲይዝ፥... የተሰጠውን እቃ ወይም ገንዘብ፥ ... ያጠፋ፥ የበላ (ሰው)።

አደራ አለ ግ አንድ ነገር እንዲደረግለት አጥብቆ አሳሰበ፥ ተማፀነ።

አደራ ከታች ቅ እንዲይዝ ወይም እንዲያስቀምጥ የተሰጠውን እቃ ወይም ገንዘብ፥... በጥንቃቄ የሚይዝ ወይም የሚጠብቅ፥ ታማኝ።

የአደራ— አስቀምጡልኝ፥ ጠብቁልኝ የተባለ (እቃ፥ ገንዘብ፥ ...)።

የአደራ ደብዳቤ ስ ከተራ መልእክት በተለየ ብልጫ የተከፈለበት፥ ደረሰኝ የሚሰጠውና ልዩ ጥንቃቄ ተደርጎለት ለተላከለት ሰው በእጁ የሚሰጥ ደብዳቤ።

አደሰ ግ 1.ጠገነ፥ አሮጌውን አዲስ እንዲሆን ወይም እንዲመስል አድርጎ ሰራ። 2.አፀዳ፥ አሳመረ። 3.እንደገና ተስማማ ወይም ተዋዋለ። *ኮንትራቱን አደሱ።* 4 አስደሰተ ወይም አዝናና። *ሙዚቃው መንፈሴን አደሰው።*

አዲስ (ብ.ቁ.**አዳዲስ**) ቅ 1.ከተሰራ ወይም ከተገዛ ያልቆየና አሮጌ ያልሆነ ወይም ያላገለገለ። 2.እንግዳ፤ ከመጣ ያልቆየ (ሰው)። 3.ከዚህ በፊት ያልተሰማ ወይም ያልተባለ ወይም ከሌላው የተለየ (ሃሳብ)።

አዲስ የመጣ ቅ ከበፊቱ የተለየ፥ አዲስ ተሰርቶ የቀረበ። *ያረገችው ጫማ አዲስ የመጣ ፋሽን ነው።*

አዲስ መስመር ስ በፅሁፍ ላይ አዲስ አንቀፅ የሚጀመርበትና ብዙውን ጊዜ ወደ ውስጥ ገባ ያለ ቦታ፤ የአንቀፅ መጀመሪያ።

አዲስ [ሃዲስ] ኪዳን ስ አራቱን ወንጌሎች፥ የሃዋርያት ስራን እንዲሁም የሃዋርያት መልእክቶችንና የዮሃንስ ራእይን የሚያጠቃልል የመፅሃፍ ቅዱስ ክፍል።

እድሳት ስ 1.ጥገና። 2.ውልን፥ ፈቃድን፥ ... የማራዘም ሁኔታ።

ታደሰ ግ አገረሸ። *ህመሙ ታደሰበት።*

አደሰ ስ ቅጠሉ ደርቆ ከተወቀጠ በኋላ ሴቶች ከቅቤ ጋር ለውሰው ፀጉራቸውን የሚቀቡት ጥሩ ሽታ ያለው የእፅዋት አይነት።

አደበ ግ ዝም አለ፥ ሠመተ፥ ረጋ።

አደብ ስ ዝምታ፥ እርጋታ፥ ትእግስት።

አደብ ገዛ ጨዋ፥ ጭምት ሆነ።

አደባባይ ስ 1.ብዙ ህዝብ የሚሰበሰብበት ወይም የሚገኝበት ቦታ። 2.ሸንጎ ወይም ችሎት የሚካሄድበት ቦታ።3. አብዛኛውን ጊዜ በከተማ መንገዶች መጋጠሚያ መሃል ላይ በክፍትነት ተትቶ አትክልት፥ ሳር...የሚተከልበት ወይም ሃውልት የሚቆምበት ቦታ።

የአደባባይ ልብስ ስ የስራ ልብስ ያልሆነ፤ የክት ልብስ።

የአደባባይ ሚስጢር ሁሉም የሚያውቀው።

አደብ "አደበ" ስር ተመ.

አደነ ግ 1.አድብቶ ወይም አሳዶ ያዘ ወይም ገደለ። 2.ከዚያም ከዚህም እያለ ሰበሰበ፥ ቃረመ። *ወሬ ሲያድን ይውላል።* 3.አሰሰ፥ ፈለገ፥ አሳደደ፥ ተከተለ። *ቤት ሲያድን ይውላል።*

አደን ስ አውሬን አሳዶ ወይም አድብቶ የመያዝ ወይም የመግደል ድርጊት።

አዳኝ ቅ 1.እንደ አንበሳ፥ ነብር፥ ... ያሉ ሃይለኛ አውሬዎችን በመግደል የሚታወቅ ሰው። 2.ፈላጊ፥ አሳሽ። *ሌባ አዳኝ፡*

አዳኝ ውሻ ስ አንድን የሚፈለግ ነገር (ለምሳሌ አውሬን፥ ወንጀለኛን፥...) በጠረን ወይም በሽታ ተከታትሎ የሚይዝ ወይም ምልክት የሚሰጥ የሰለጠነ ውሻ፤ ሰላግ ውሻም ይባላል።

ታደነ ግ 1. ተፈለገ፥ ክትትል ተደረገበት። 2.ተፈልጎ እንዲያዝና በቁጥጥር ስር እንዲውል ተደረገ (ሰው)።

አደንጓሬ ስ ቅርፁ ባቄላ የሚመስል ነገር ግን ጠፍጠፍ ያለና የተለያየ ቀለም ያለው ባለሃረግ የአበባ እህል።

አደይ [አበባ] ስ በመስከረም ወር የሚፈነዳ ብጫ ቀለም አበባ።

አደገ ግ 1.ቁመቱ ጨመረ፥ ተለቀ፡ተመነደገ። 2. ጨመረ፥ በረከተ፥ በዛ። 3. ላቀ፥ ከፍ አለ (በደረጃ፥ በሃብት፥በስልጣኔ ...)።

ማደጎ ቅ በተለያየ ምክንያት ከወላጆቹ ተነጥሎ ባእድ ወይም ዘመድ ቤት ያደገ።

አዳጋ ቅ ከፍ ያለ፥ ዳገታማ። *አዳጋ ቦታ፡*

እድገት ስ 1.ከፍ ወይም ላቅ ያለ ደረጃ። 2.ብልፅግና ወይም ሃብት። 3.የቁመት መጨመር።

ታዳጊ ቅ 1.ቶሎ ቶሎ የሚያድግ። 2. ከ7 14 አመት ባለው የእድሜ ክልል ውስጥ ያለ ወጣት (ልጅ)።

ታዳጊ አገሮች ስ በመልማት ላይ ያሉ አገሮች።

አሳደገ ግ ተንከባክቦ ለትልቅነት አበቃ ወይም አደረሰ።

አሳዳጊ ቅ ልጆችን በመንከባከብ የሚያሳድግ፥ ወላጅ፥ ሞግዚት።

አሳዳጊ የበደለው (ስድብ) ያልተቀጣ፥ መረን አደግ፥ ባለጌ (ልጅ)።

አስተዳደግ ስ የእድገት ሁኔታ። *የልጁ አስተዳደግ ምቾት ያለው ነበር።*

አደጋ ስ ድንገት ሳይታሰብ የሚደርስ መጥፎ አጋጣሚ ወይም ጉዳት።

አደጋ ላይ ጣለ አደጋ እንዲደርስበት አደረገ።

አደጋ ወደቀበት አደጋ አጋጠመው።

አደጋ ጣለ አድፍጦ በሌላው ላይ አደጋ ወይም ድንገተኛ ጉዳት አደረሰ።

አደገኛ ቅ 1.ጉዳት የሚያስከትል ወይም የሚያደርስ። 2.ሃይለኛ፥ ብርቱ፥ ጠንካራ። 3.ተንኮለኛ፥ ክፉ።

አደፈ ግ ቆሸሸ፥ እድፍ ያዘ።

አዳፋ ቅ የቆሸሸ።

እድፍ ስ ቆሻሻ፥ ጭቅቅት።

እድፋም ቅ (ስድብ) ቆሻሻ፥ ጭቅቅት ያለበት ወይም የበዛበት።

አደፍ ስ የሴቶች የወር አበባ።

አዱኛ ስ ሃብት፥ ብልፅግና።

አዲስ "አደሰ" ስር ተመ.

አዳል በግ ስ በጣም ቆላ በሆነ አካባቢ የሚረባና ላቱ ሰፊ የሆነ የበግ አይነት።

አዳሜ(የን.አነ.) ስ ህዝብ፥ የአዳም ዘር። *አዳሜን ስቀልብ ልኖር ነው እንዴ?*

አዳም ሃሙስ ስ ከፋሲካ በኋላ ለሚመጣው የመጀመሪያው ሃሙስ የተሰጠ ስም።

አዳሪ "አደረ" ስር ተመ.

አዳራሽ ስ 1.ለስብሰባ፥ ለትርኢት ማሳያ፥ ... የሚያገለግልና ብዙ ሰው የሚይዝ ሰፊ ቤት። 2.ሰፊ፥ ትልቅ (ለቤት)።

አዳር "አደረ" ስር ተመ.

አደሲቁኒ ስ ጥቁር መልክ ያለው፥ ከአይጥ በለጥ የሚልና አይጥ መሰል የዱር አውሬ።

አዳኝ "ዳኘ" ስር ተመ.

አዳኝ "አደነ" ስር ተመ.

አዳይ "አደለ" ስር ተመ.

አዳጊ "አደገ" ስር ተመ.

አዳፋ "አደፈ" ስር ተመ.

አዳፍኔ "ደፈነ" ስር ተመ.

አድለቀለቀ ግ አናወጠ፥ አንቀጠቀጠ።

አድልዎ "*ዳላ" ስር ተመ.

አድመኛ "አደመ¹" ስር ተመ.

አድማ ዝ.ከ.

አድማስ ስ ሰማይና ምድር የተገናኙበትና የምድር ዳር ድንበር መስሎ የሚታይ ቦታ።

አድራሻ "ደረሰ" ስር ተመ.

አድርባይ "አደረ" ስር ተመ.

አድባር "ደበረ¹" ስር ተመ.

አድናቆት "ደነቀ" ስር ተመ.

አዶ ስ እንደዝሆንና አንበሳ ያሉ ሃይለኛ አውሬዎችን የገደለ አዳኝ ያደርገው የነበረ ከዝሆን ከቱ የሚሰራ አምባር ወይም ሎቲ።

አዶቀረ ግ ሲጠራ ጆሮው እየሰማ እንዳልሰማ በመምሰል ዝም አለ ወይም መልስ ሳይሰጥ ቀረ፤ አዶበረ።

አዶወሸባዬ ስ አውሬ (አንበሳ፣ ዝሆን፣...) ሲገደል አዳኝ ይዘፈን የነበረ ዘፈን።

አጀለ ግ 1.የደረቀ ወይም የገረረ ቆዳን ቀባት ቀብቶ በቅጠል በመጠቅለልና ድንጋይ ጭኖ በማስንበት እንዲለዘብ ወይም እንዲለሰልስ አደረገ። 2.የተሰበረ ወይም ቦታውን የለቀቀ አጥንትን ለማስተካከል ወይም ለመጠገን እንዲያመች አብሽ ቀብቶና በጨርቅ ጠቅልሎ አስነበተ። 3.ረዘም ላለ ጊዜ አንድ ቦታ ላይ አስቀመጠ፤ ወዘፈ።

እጅላት የአስተጃጀል ሁኔታ ወይም መንገድ።

ታጀለ ግ ከአንድ ቦታ ሳይንቀሳቀስ ለረጅም ጊዜ ቆየ። *ስንት ሰዓት ሙሉ እዚህ ታጅዬ እቀመጣለሁ!*

አጀረ ግ ነፋ፤ ቀበተተ (ሆድን)።

አጀበ ግ 1.ከበበ፤ ከግራ ከቀኝ፤ ከፊት ከሃላ በመሆን አብሮ ሄደ፤ ተከተለ። 2.አንድ ቦታ ላይ ሰበሰበ ወይም አከማቸ።

አጀብ ስ 1.የማጀብ ስራ። 2.አጃቢ።

አጃቢ ስ 1.ከንጉስ፣ ከባለስልጣን፣ ... ጋር ወደ ተለያየ ቦታ አብሮ የሚሄድ፤ ጠባቂ። 2.የተለያዩ የሙዚቃ መሳሪያዎችን በመያዝ ድምፃዊውን (ዘፋኙን) የሚያዳምቅ የኪነት ቡድን።

አጀብ ግሩም፤ድንቅ፤ጉድ ለማለት የሚነገር ቃል።

አጀንዳ ስ 1.አድራሻና ከእለት እስከ አመት የተከናወኑ ወይም የሚከናወኑ ጉዳዮች የሚመዘገቡበት የቀን መቁጠሪያ ያለበት ማስታወሻ ደብተር። 2.ለስብሰባ ወይም ለውይይት የሚቀርቡና በተራ ቁጥር የተዘረዘሩ ርእሰ ጉዳዮች።

አጃ ስ የተነባበረ ሽፋንና ምርቅ ያለው ስንዴ የሚመስል እህል።

አጃቢ "አጀበ" ስር ተመ.

አጅሬ ቅ ጎበዙ፣ የማይሳነው፤ የታወቀው (በጥሩም በመጥፎም)። *አጅሬ ስራውን በጠዋት ጨርሶ ሄደ/ቤቱ ክፍት ከሆነ አጅሬ ገብቶ ይሰርቃል።*

አገለ¹ ግ ኮተኮተ፤ አፈር አስታቀፈ (ተክልን)።

እግል ስ የተኮተኮተና ስሩ አፈር የታቀፈ (አትክልት)።

አገለ² ግ አገረሸ፤ መልሶ አመመ (ቁጥኝ)።

እግል ስ የአገረሸ የቁጥኝ በሽታ።

አገልግል ስ በውስጡ ምግብ ወይም የተለያየ እቃ ለመያዝ የሚያገለግል ባለመክደኛ የበፌት እቃ።(ስእሉን የበፌት እቃ ስር ተመ.)

አገልግሎት "*ገለገለ" ስር ተመ.

አገመ ግ የታመመን ሰው ገላ በጥቶ የተበከለውን ደም በዋግምት ስቦ አወጣ።

አገም ጠቀም አደረገ 1.በአንድ በኩል የጠቀመ አስመስሎ በሌላ በኩል ጎዳ ። 2.ጥሩ ወይም መጥፎ የማይባል ስራ ሰራ።

ዋግምት በፊደል ተራው ተመ.

አገመደደ ግ አኮሳተረ፤ አጨማደደ፤ አጠቆረ (ፊትን)።

አገር "ሃገር"ን ተመ.

አገተ ግ 1.የተከለከለ ቦታ የገባና አትክልት፤ ሳር፤ አዝመራ፤... የበላን፤ ያበላሸን ከብት ይዞ አሰረ ወይም አጎረ። 2.የዋስን ንብረት በእዳ ያዘ ወይም ወሰደ።3. አንድን ጉዳይ በማስገደድ ለማስፈፀምሰዎችን በመያዣነት ያዘ።

አጋች ቅ 1. በተከለከለ ክልል ውስጥ የገቡ ከብቶችን ወይም ዋስ ሆኖ ግዴታውን ያልተወጣ ሰውን በመያዝ ወይም በማሰር አስፈላጊውን እርምጃ የሚወስድ ወይም ለማስወሰድ የሚችል (ሰው)። 2. አንድን ጉዳይ አስገድዶ ለማስፈጸም ሰዎችን በማያዣነት የያዘ።

እግት ስ በህግ የተያዘ (ከብት፣ እቃ፣ ንብረት፣...)።

ታገተ ግ 1. በህግ ተያዘ (ዋስ፣ ንብረት፣...)። 2.በመያዣነት ተያዘ።

ታጋች ቅ በዋስትና ምክንያት ወይም በለውጡ ጥቅም ለማግኘት ሲባል በህግ ወይም በህገወጥ መንገድ በቁጥጥር ስር እንዲውል የተደረገ ሰው፣ ንብረት፣...።

አገነደረ "*ገነደረ" ስር ተመ.

አገና (አጋና) ስ በሻጭና በገዢ መካከል የሚደረግ ስምምነት፤ ውል።

አገና ተማታ ሻጭና ገዢ ተስማማ፤ ተሻኮተ።

አገና አማታ ሻጭና ገዢን አስማማ፤አሻኮተ።

አገዘ ግ ረዳ፡ ደገፈ፡ ተባበረ።

አጋዥ ቅ ረዳት፡ ደጋፊ።

አጋዥ ግንድ ስ ከፊት ግንድ ቀጥሎ የሚገኘና የፊት ግንድ ረዳት የሆነ የሽማኔ እቃ።

እገዛ ስ እርዳታ።

ታገዘ ግ ተረዳ፡ ተደገፈ።

ተጋገዘ ተረዳዳ፡ ተባበረ (እርስ በእርስ)።

አገደ ግ 1.ከለከለ፡ አቆመ። 2.ገደበ፡ ከተረ። 3.ከብትን ጠበቀ።

አጋጅ ቅ እረኛ ወይም ጠባቂ።

እገዳ ስ 1.ከብት ጥበቃ። 2.ማእቀብ።

እግድ ቅ 1.ክልክል፡ ዝግ። 2.ክትር፡ ግድብ።

አገደደ ግ 1.አዞረ፡ ጠመዘዘ። *አንገቱን አገደደ።* 2.ጠመመ፡ ወለገደ።

አገዳ ስ 1.እንደ በቆሎ፡ ማሽላ፡ ... ያሉ የአዝርእት እህሎች ግንድ። 2.ሸንኮራ አገዳ። 3.ከጉልበት እስከ ቁርጭምጭሚት ወይም ከክርን እስከ አምባር መዋያ ያለው የእግርና የእጅ ክፍል።

አገዳ ሰበር ስ የአሞራ አይነት፡ ወድቆ የሚያገኘውን የበሬ ቅልጥም መቅን ለመብላት ሲል ወደ ሰማይ አውጥቶ ድንጋይ ላይ በመጣል ስለሚሰብር ቅልጥም ሰባሪ እየተባለም ይጠራል።

የአገዳ እህል ስ እንደ ማሽላ፡ በቆሎ፡ ... ሁሉ አገዳ ያለው የእህል አይነት።

አገጭ ስ በታችኛው ከንፈር አካባቢ የሚገኝ የሰውነት ክፍል(ስእሉን ራስ ስር ተመ.)።

አገጫም ቅ (ስድብ) አገጩ ትልቅ የሆነ ሰው፡ማንቋላም።

አጉል "አጎለ" ስር ተመ.

አጉመተመተ "አጉተመተመ"ን ተመ.

አጉራ "አጎረ" ስር ተመ.

አጉራዶ "ጎረዶ" ስር ተመ.

አጉተመተመ(አጉመተመተ) ግ አጉረመረመ።

አጉተምታሚ (አጉመትማች) ቅ አጉረምራሚ።

አጋ

አጋ ለየ በተለ ጊዜ ወገን፡ አጋር፡ አንጃ ለየ፡ የአንዱ ወገን ከሌላው ተለይቶ በመተባበር በአንድ በኩል ሆነ።

አጋሙዳ ቅ (ስድብ) ሆዳም፡ ከርሳም።

አጋሚዶ ስ በበዝበዛ በመንግስት ላይ ያመፀ፡ ዱር የገባ ወንበዴ፡ ሽፍታ።

አጋም ስ ፍሬው የሚበላ እሾሃም የእፅዋት አይነት።

አጋም መሰለ 1.ቀላ ያለ መልክ ያዘ። 2.በሰለ፡ ጎመራ።

አጋም አዙርበት በአጋም ተነቀስ (ጥርስህን)።

አጋሬ ስ ዝበሉ።

አጋር ስ ረዳት፡ ተባባሪ፡ ግብረ አበር።

አጋሰስ ስ 1.ለእቃ መጫኛ የሚያገለግል በቅሎ ወይም ፈረስ። 2.(ስድብ ዘይ.) ሀ. ሆዳም፡ በልቶ የማይጠግብ። ለ. ገልቱ፡ ሙያ የሌለው።

አጋች "አገተ" ስር ተመ.

አጋንንት "ጋኔን"ን ተመ.

አጋዘን ስ ምድቡ በከብት ዘር ውስጥ የሆነ፡ ጠምዛዛና ረጃጅም ቀንዶች ያሉት ቅጠላ ቅጠል የሚመገብ የዱር እንስሳ(ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።

አጋዥ "አገዘ" ስር ተመ.

አጋይ "ሃጋይ"ን ተመ.

አጋደደ ግ አበደረ፡ አዋሰ።

አጋጅ "አገደ" ስር ተመ.

አጋፈረ ግ በቤተመንግስት፡ በግብር የታ፡... በር ላይ ቆሞ የሚገቡትንና የሚወጡትን ሰው አስተናበረ፡ አስተናገደ።

አጋፋሪ ቅ አስተናባሪ (ብዙውን ጊዜ በግብር ወይም በቤተመንግስት በር ላይ በመቆም ስርአት የሚያስከብር)።

አጋፈጠ ግ 1.ተረከዞቹ ላይ ቁጢጥ ብሎ በመቀመጥና በውስጥ በእግሮቹ ጣቶች መሬት በመርገጥ እጆቹን እጉልበቶቹ ላይ አድርጎ እፍ እፍ የሚል ድምፅ እያሰማ ወደ ላይ እንጣጥ እንጣጥ በማለት እየዘለለ ተጫወተ። 2.ያለ ስራ ከወዲያ ወዲህ ሮጠ፡ አደሸደሸ።

አጋፋሪ "አጋፈረ" ስር ተመ.

አግራፍ ስ ወረቀቶችን በአንድነት አጣብቆ ለመያዝ የሚያገለግል መንታ ጫፍ ያለው ሽቦ ወይም ብረት።

አግራፍ

አግባብ "ገባ" ስር ተመ.

አግቦ ስ አሽሙር፡ ሽሙጥ።

አግቦኛ ቅ አሽሟጣጭ፡ አሽሙረኛ።

አግድመት "ገደመ" ስር ተመ.

አግድም ዝ.ከ.

አግድዋሞሽ ዝ.ከ.

አጎለ ግ አወከ፡ አስቸገረ፡ መሰናከል ሆነ።

አጉል (አንጉል) ቅ የማይረባ፡ መጥፎ።

ታጎለ ግ ተዳፈነ፡ ተቋረጠ(ግብር፡ቅዳሴ፡ ...)።

ተንጎለ ግ ተሰናከለ፤ መደረግ የሚገባው ሳይደረግ ወይም ሳይከናወን ቀረ።

አስታጎለ ግ አዳፈነ፤ አቋረጠ (ቅዳሴን፤ ግብርን፣ ...)።

አጎመ ግ አጎነቆለ፤ አጎመጎመ።

አጎረ ግ 1.ከብቶችን ወደ በረት አስገብቶ በሩን ዘጋ። 2.አከማቸ፤ ሰበሰበ፤ አከተ።

አጉራ ስ ከብቶች እንዳይወጡ በበረት በር ላይ የሚጋደም እንጨት።

አጉራህ ጠናኝ አለ ተረታሁ፤ ተሸነፍኩ አለ (በመጫወት ጊዜ)።

አጉራ ዘለል ቅ (ስድብ) ባለጌ፤ ስድ፤ ስነ ስርአት የጎደለው፣ ጋጠ ወጥ።

አጎበር ስ 1.አቧራን ወይም ነፍሳትን ለመከላከል በአልጋ ወይም በዙፋን ዙሪያ ላይ እንደ ድንኳን የሚዘረጋ መጋረጃ። 2.በአልጋ ቅርፅ የተሰራ፣ በላዩ ላይ እንደ ጣሪያ የሚያገለግሉ ቅስቶች የተደረጉበትና በንምጃ ወይም በጨርቅ የተሸፈነ የራስ ወይም የበሽተኛ ማጓጓዣ። 3.ግድግዳውና ጣሪያው በጥንት በሳቸው እንጨቶች በቅስት መልክ የሚሰራ ጎጆ፤ ቀልስ።

አጎበጎበ ግ አሸቀበበ፤ አቃለበ።

አጎብጋቢ ቅ (ስድብ) አሸቃባጭ፤ ሊቀላዋጭ፣ አጨብጫቢ።

አጎዛ ስ 1.ተሰፍቶ ለልብስነት ወይም ለንጣፍ የሚያገለግል የበግ ወይም የፍየል ቆዳ። 2.(ስድብ ዘይ.) ሞኝ፤ ጅል።

አጎዳ ስ የከብት ኩሱ። *ከብቱ ሲነዳ አጎዳው ከሩቅ ይሸት ነበር።*

አጎዶ[1] ስ 1.እንደ ክሰል፤ ወርቅ፤... ያለ ማእድን የሚያጣሩበት ጉድጓድ። ቅ (ስድብ) መልከ ጥፉ።

አጎዶ[2] ስ የላም በረት (ጎንደር)።

አጎት ስ የአባት ወይም የእናት ወንድም።

አጎጠጎጤ "*ጎጠጎጠ" ስር ተመ.

አጎጤ ዝ.ክ.

አኅመጠ "ኅመጠ" ስር ተመ.

አኅራ ግ ተደጋጋሚ ጩህት አሰማ (ዛር የሰፈረበት ሰው)።

አኅት ስ አሬራ ወይም ወተት ከተፈላ በሁዋላ አይቡ ሲዘቅጥ ከላይ ጠልሎ የሚቀረው ውሃ መሰል ወተት ወይም ነጭ ፈሳሽ።

አኅጉል "አጎለ" ስር ተመ.

አኅጎት (ኅጎት) ስ ብዙውን ጊዜ በፊት ወይም በእጅ ላይ የሚታይ እንደ ጭርት ያለ የቆዳ በሽታ።

አጠረ[1] ግ 1.ቁመቱ ወይም ርዝመቱ ተቀነሰ፣ አጭር ሆነ፤ አነሰ። 2.አጠጠ፣ ቸገረ (ገንዘብ፣ ጊዜ፣ ...)።

አጣራ ቅ አጭር ወይም ቁመቱ ዘለግ ያላለ።

አጭር (ብ.ቁ.**አጫጭር**) ቅ 1. ርዝመቱ ወይም ቁመቱ ያነሰ። 2.ድንክ፤ ድውይ። 3.የተወሰነ፤ ጥቂት (ጊዜ፣...)።

በአጭር ቀረ 1.ያለ እድሜው በቶሎ ሞተ። 2.እድገቱ ተደናቀፈ ፣ ተቀጨ።

በአጭር ቅር (እር.) አትደግ፣ ያለእድሜህ ቶሎ ይግደልህ።

በአጭር ታጠቀ ከልብ ተዘጋጀ (ለስራ፣ ለጉዞ፤ ...)።

አጭር ልቦለድ ስ በጥቂት ገፀ ባህርያትና በአጠረ ጊዜ ተመጥኖ በአንድ ታሪክና በዚያ ታሪክ ነጠላ ውጤት ላይ የሚያተኩር፣ በስድ ንባብ የተቀነባበረ የስነፅሁፍ አይነት።

አጭር ቃል ስ ሃተታ የሌለበት ንግግር፣ ፍሬ ነገሩ ብቻ።

አጭሬ ስ 1.ቁመቱ አጭር የዘንጋዳ አይነት። 2.ከዶሮ ስጋ ብልት የጭኑ ክፍል።

እጥረት ስ የአንድ ነገር ማነስ፣ በበቂ ሁኔታ ወይም በብዛት አለመገኘት።

እጥር ምጥን ያለ ሳያጥር ሳይረዝም፣ ሳይበዛ ሳያንስ በልክ የሆነ፣ የተመጠነ።

አጠረ[2] ግ1. በእንጨት፣ በድንጋይ፣ በእሾህ፣ ... የቤትን የአዝርእትን፣ ... ዙሪያ ከለለ ወይም ጋረደ።2. ከለከለ፣ዘጋ፣አላሳልፍ አለ።

አጥር ስ በእንጨት ወይም በድንጋይ ወይም በእሾህ፣... በቤት፣ በአዝርእት፣... ዙሪያ የሚደረግ ከለላ፤ ገረገራ፤ ቅጥር።

አጥር ቅጥር ስ የቤት አጥርና ግቢ።

አጥር ግቢ ስ ከአጥር በውስጥ በኩል ያለ የቤት አካባቢ፣ ግቢ።

አጠበ ግ 1. አፀዳ፣ አጠራ፣ አነፃ፣ ቆሻሻን አስለቀቀ ወይም አስወገደ (በውሃ፣ በሳሙና፣...)። 2.ሙጥጥ አድርጎ ወሰደ ወይም ሰረቀ (ንብረትን)። 3. ከፎቶግራፍ ፊልም ላይ ምስልን በወረቀት ላይ አወጣ፣ አተመ።

ቢያጥቡት አይጠራ 1.ቂመኛ፣ ነገር በሆዱ የሚይዝ (ሰው)። 2.እንከኑ፣ ጉድለቱ፣... የማያጣው።

እጣቢ ስ ከሚታጠብ ነገር ላይ የሚወጣ እድፍ ወይም ቆሻሻ።

እጥብጣቢ ዝ.ክ.

እጥብጥብ አለ ግ 1.ተጣጠበ፣ ፀዳ። 2.አለቀ፣ ተሟጠጠ፣ ባዶ ሆነ።

እጥብጥብ አድርጎ ወሰደ ምንም ሳያስቀር ሙጥጥ አድርጎ ወሰደ።

ታጠበ ግ 1. ከቆሻሻ ጠራ፣ ፀዳ፣ ነፃ።

2. በኬሚካል አማካይነት በፎቶግራፍ ፊልም ላይ ያለ ምስል እንዲታይ ማድረግ፡ ማጥቆር።

ታጥቦ ጭቃ ስ አንድን አጉል ልማድ ወይም ኢ.ተ.ድርጊ፡ አይሆንም የተባሉትን ነገር ለጊዜው ከተው በኋላ እንደገና ወደዚያው የመመለስ ድርጊት።

መታጠቢያ ስ ገላን ሰውነትን፡ ለመታጠብ የሚያገለግል (ውሃ፡ ሳሙና፡ ዕቃ)።

መታጠቢያ ቤት ስ ገላን ሰውነትን ለመታጠቢያ የሚያገለግል ቤት ወይም ክፍል።

ተጣጠበ ግ ተለቃለቀ፡ ታጠበ።

ኣስታጠበ ግ እጅ ላይ ውሃ በመጨመር እንዲታጠብ አደረገ።

ኣጠነ ግ 1. እንደ እጣን፡ ስራስር፡ ቅጠላ ቅጠል፡ ... ያሉ ነገሮችን እሳት ላይ አድርጎ በማጨስ መዓዛው እንዲሸት ወይም እንዲያውድ አደረገ። 2.የታጠበ ልብስ ወይም የወተት እቃ ጥሩ መዓዛ እንዲያገኝ የማእጠንት ጢስ እንዲጨስበት አደረገ።

ኣጣኝ ስ ቤተ ክርስቲያንን ወይም ቤተ ዘሉትን የሚያጥን ቄስ።

ዮጣኝ ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ዋናው ተገባር በተበላ በሰሰተኛው ቀን ለተወሰኑ ካህናት ብቻ ይደረግ የነበረ መጠነኛ ግብዣ።

እጣን ስ ጢሱ ጥሩ መዓዛ ያለው የእንጨት ሙጫ።

እጣን ሞገር ስ ከቅዳሴ መጨረሻ ገደማ ላይ የሚባል የማእጠ ቅኔ።

ማእጠንት (ማጠንት) ስ እንደ ሰንቡል፡ ኡድ፥ ጥንጅት፡ ... ያሉና ጥሩ መዓዛ ያለው የጢስ እንጨት።

ኣሳጠነ ግ እንዲታጠን አደረገ ወይም አስደረገ።

ኣጠናቀረ "*ጠነቀረ" ስር ተመ.

እጠናገረ "ጠነገረ"** ስር ተመ.

ኣጠድ "እፀድ"ን ተመ.

ኣጠገብ ተው.ግ አቅራቢያ።

ኣጠገብ ለኣጠገብ ቅርብ ለቅርብ፥ ያልተ ራራቀ።

ኣጠጠ ግ እነሰ፥ ጎደለ።

እጥጥ ሙጥጥ ኣለ ግ አለቀ፡ ተሟጠጠ።

ኣጠፈ ግ 1.ስፋት ወይም እርዝመት ያለውን ነገር (ጋቢ፥ ነጠላ፥ ...) ደጋግሞ በመቀልበስ መጠኑ አነስ እንዲል አደረገ። 2.ቆለመመ፡ አስጎነበሰ። *ምስማሩን ኣጠፈው*። 3.ዘጋ፥ ከደነ (መፅሃፍን)። 4.ያለውን ቁጥር ያህል መጠኑ ጨመረ፡ አጠፌታ አደረገ።

ማጠፊያ ስ መዝጊያንና መስኮትን ከመቃን ጋር ለማያያዝና ወዲያና ወዲህ ለማንቀሳቀስ (ለመዝጋትና ለመክፈት) የሚያገለግል ብረት።

ኣጠፌታ ስ እጥፍ።

እጥፍ ቅ ድርብ፡ ጥንድ፡ ነጠላ ያልሆነ።

እጥፍ ድርብ ቅ ኣያሌ፡ ብዙ።

እጥፋት ስ ቅልብሰት፡ ስብራት (የልብስ)።

ታጠፈ ግ 1.ቀጥታውን መንገድ ትቶ ወደ ጎን አመራ። 2.ተቀነፈ፡ ተቀለሰ። 3.ተጎነበሰ፡ ተቆለመመ።

ታጣፊ ቅ ሊያጥር ወይም ሊተጣጠፍ፡ ሊቆለመም የሚችል (አልጋ፡ ወንበር፡ ብረት፡ ...)።

ተጣጠፈ ግ ተኮረመተ፡ ተጨበበ።

ኣጣ ግ 1.ተቸገረ፡ ደሀየ። 2.የፈለገውን ወይም የተመኘውን ሳያገኝ ቀረ። 3.ረሳ፡ ጠፋበት፡ ሳያውቀው ቀረ። *የሚያውቀውን መልስ አጣው*።

ኣጣ ነጣ በጣም ተቸገረ፡ ደሀየ።

እጦት ስ ችግር፡ ድህነት።

እጦተኛ ቅ ችግረኛ፡ ደሃ።

ታጣ ግ 1.ጠፋ፡ ሳይገኝ ቀረ። 2.ተረሳ፡ ተዘነጋ።

ተጣጣ(ተጣጡ) ግ 1. ተረሳሳ፡ አንዱ ሌላውን ማስታወስ ተሳነው፡ ተጠፋፋ። 2.ሳይገናኙ ቀሩ።

ኣሳጣ ግ ከለከለ፡ ነሳ።

ኣጣሪ "ጠራ^{2}" ስር ተመ.

እጣራ ዝ .ከ.

ኣጣራ "ኣጠረ^{1}" ስር ተመ.

ኣጣቆስ ግ ኣሳበቀ፡ ኣዋሸከ።

ኣጣቢ "ኣጠበ" ስር ተመ.

ኣጣና ስ የተለያየ አገልግሎት የሚሰጥ፡ መጠነኛ ውፍረት ያለውና መለል ብሎ ዘለግ ያለ ድፍን እንጨት(ብዙውን ጊዜ ባህርዛፍ)።

ኣጣኝ "ኣጠነ" ስር ተመ.

ኣጣጥ ስ ትንንሽ እሾህ ያለው የቁጥቋጦ ዛፍ አይነት።

ኣጣፋ ግ 1.ጋቢን፡ ነጠላን፥ ኩታን፥... ከአንደኛው ትከሻው እስከ ሁለተኛው ትከሻው በመዘርጋት ሰውነቱን ሸፈነ፥ አለበሰ። 2.መካፈል የሚችሉ ቁጥሮችን አካፈለ (ሂሳብ)።

ማጣፊያ ስ የኩታ፥ የጃኖ ቁመት ወይም ርዝመት።

ማጣፊያ ኣጠረው የሚናገረውን ወይም የሚያደርገውን ወይም የሚሆነውን አጣ፥ ተቸገረ፥ ዘዴ፥ ብልሃት ጠፋው፡ አጠረው።

አጣፊኝ ስ በአንገት ላይ የሚለበስ ባለ አንድ ፈርጅ ነጠላ።

አጤ "**አፄ**"ን ተመ.

አጥሚት ስ በአብዛኛው የአጃ ወይም የገብስ ወይም የስንዴ ዱቄትን በውሃ በጥብጦ እሳት ላይ በማንተክተክ (በማፍላት) በፈሳሽ መልክ የሚዘጋጅ ምግብ፣ ሙቅ፣ እንትክትክ።

አጥር "**አጠረ**^{2}" ስር ተመ.

አጥቅ "**አፅቅ**" ን ተመ.

አጥቢያ^{1} ስ አካባቢ፣ ሰበካ፣ ቀበሌ።

አጥቢያ ዳኛ ስ በአንድ በተወሰነ አካባቢ በዳኝነት እንዲያገለግል ከህዝብ መካከል ተመርጦ የተሰየመ ዳኛ።

አጥቢያ^{2} "**ጠባ**^{2}" ስር ተመ.

አጥናፍ "**ጠነፍ**" ስር ተመ.

አጥንት ስ በስጋና በቆዳ የተሸፈነውና ጠንካራ የሆነው የአካል ክፍል።

አጥንተ ሰባራ ቅ ዘሩ ወይም ትውልዱ ከሃብታም፣ ከባላባት፣ ከጨዋ ዘር ያልሆነ ለማለት በቀድሞ ጊዜ ይነገር የነበረ ቃል።

አጥንት የሚሰብር ስሜት የሚጎዳ፣ ዘርን የሚነካ መጥፎ ስድብ ወይም ንግግር ።

አጥንቱ የወጣ በጣም የከሳ፣ አጥንቱ የገጠጠ።

የአጥንት ልጅ መደበኛ የመወለጃ ጊዜውን አሳልፎ የተወለደ ልጅ።

የአጥንት ፍላጭ የስጋ ቁራጭ ከአብራኩ የወጣ የገዛ ልጅ።

አጥግቢኝ "**ጠገበ**" ስር ተመ.

አጥፍ "**አፅፍ**"ን ተመ.

አጨ ግ 1.መለመለ፣ መረጠ (ለሹመት፣ ለእድገት)። 2.ቃል ኪዳን አሰረ፣ ለትዳር መረጠ፣ ተዋዋለ።

ማጫ ስ ለሚስትነት ለተመረጠችው ልጅ የሚሰጥ ገንዘብ፣ ከብት፣ ...።

አጭታ ስ አንድን ሴት ልጅ ለትዳር መርጦ ወይም መልምሎ በቃል ኪዳን ያስቀመጠ ሰው።

እጩ ቅ ለአንድ ጉዳይ (ለሹመት፣ ለስራ፣ ...) የተመለመለ ወይም የታሰበ (ሰው)።

እጮኛ ስ ቃል ኪዳን የገባ ወይም ቀለበት ያሰረ የወደፊት የትዳር ጓደኛ።

አጨለገ ግ 1.በአንድ አይኑ በቀዳዳ ተመለከተ፣ አጮለቀ፣ አንጣጠረ። 2. አታሎ ወሰደ፣ ሰረቀ።

አጭልግ (አጭላጊ) ቅ አታላይ፣ ሌባ።

አጨቀ ግ በብዛት አመቀ፣ ከተተ፣ ጠመረ።

ታጨቀ ግ በብዛት ተከተተ፣ ታመቀ።

አጨናፈረ "**ጨነፈረ**" ስር ተመ.

አጨደ ግ በብዛት በመያዝ ከስር ቆረጠ (ሳርን፣ ሰብልን፣...)።

አጨደው ጨረሰው፣ ፈጀው። *ረሃብ ህዝቡን አጨደው።*

ማጭድ ስ ከብረት የሚሰራ፣ እንደ ደጋን ጎበጥ ብሎ በአንድ በኩል ከስር እስከ ጫፍ ስለት ያለውና ሳርን፣ ሰብልን፣... ለማጨድ የሚያገለግል ባለእጀታ የግብርና መሳሪያ።



ማጭድ

አጨዳ ስ የማጨድ ተግባር።

አጫዳ ስ (ሀይ፣ ስድብ) እግረ ሽፋፋ።

አጭልግ "**አጨለገ**" ስር ተመ.

አጭሬ "**አጠረ**^{1}" ስር ተመ.

አጭር ዝ.ከ.

አጭታ "**አጨ**" ስር ተመ.

አጮለ "***ጮለ**" ስር ተመ.

አጮለቀ ግ አይኑን ላባዩን እያለ ቀስ ብሎ በስርቆት ተመለከተ።

አጮልቆ አየ ዝ.ከ.

አፀድ (አጠድ) ስ 1.የአትክልት ወይም የዛፍ ቦታ። 2.በቤተ ክርስቲያን ዙሪያ ያለ አትክልት ወይም ዛፍ።

አፀደ ህፃናት ስ ህፃናትን ለመደበኛ ትምህርት የሚያዘጋጅ ትምህርት ቤት።

አፀደ ነፍስ ስ ሰው ከሞተ በኋላ ነፍሱ በሰማይ ትኖርበታለች ተብሎ የሚታመንበት ቦታ።

አፀፋ ስ ምላሽ።

አፄ (አጤ) ቅ በንጉስ የተፀውኦ ስም ላይ ተደርቦ በመነገር ንጉሳዊ ማእረግን የሚገልፅ ቃል። *አፄ ዮሃንስ፣ አፄ ሚኒሊክ፣ አፄ ሃይለ ሥላሴ።*

አፅም ስ አጥንት።

አፅሙ የረገፈበት የተቀበረበት።

አፅመ ርስት የ"ርስት"ን 1ኛ ፍቺ ተመ.

አፅቅ (አጥቅ) ስ 1. የዛፍ

አፅም

ወይም የተክል ቅርንጫፍ ኣናት፣ ጫፍጫፉ። 2.ከአንጓ እስከ አንጓ ያለ የጣት ክፍል፤ ቅልጥም።

አፅናፍ "ጠንፍ" ስር **"እጥናፍ"**ን ተመ.

አፅፍ (እጥፍ) ስ ከአጋዘን ወይም ከበሬ ቆዳ የሚሰራ የመነኩሴ ልብስ።

አፈለ ግ 1.ጎለመሰ፣ ጎረመሰ። 2.ጠነከረ፥ በረታ፥ ጎበዘ።

አፍላ ቅ 1.ጎረምሳ፣ ወጣት። 2.ያልዘገየ፥ ያልቆየ፣ ትኩስ።

አፍላ እንቅልፍ ከጀመረ ብዙም ያልቆየ ሃይለኛ እንቅልፍ።

አፍለኛ ቅ 1.ጎረምሳ፥ ወጣት። 2.አፍለኝ።

አፍለኝ (አፍለኛ) ቅ ከአልቦካ ሊጥ የተጋገረ እንጀራ።

አፈላማ ስ አትክልቱ ወይም ሰብሉ በከብት የተበላበት ሰው ከባለከብቱ የሚቀበለው ገንዘብ።

አፈሙዝ ስ የጠመንጃ፣ የሽጉጥ፥ ... አፍ።

አፈረ ግ 1.በአሳፋሪ ድርጊቱ ተዋረደ፥ ቀለለ። 2.ፈራ፥ ተሸኮረመመ። 3.ጠወለገ፥ ደረቀ። 4.ሸፈጠ፥ ከዳ፥ አሌ አለ፣ ቃሉን ለወጠ። 5.እያነሰ ወይም እየጎደለ ሄደ (ምንጭ)።

ማፈሪያ ስ አሳፋሪ፥ አዋራጅ።

እፍረት (ሃፍረት፥ ሀፍረት) ስ 1.ውርደት፥ ቅሌት፣ ነውር። 2.ፍርሃት፥ መሽኮርመም። 3.ሽፍጥ።

እፍረቱን ጣለ 1.እርቃኑን ሆነ። 2.ማፈር መፍራቱን ተወ፣ አይኑ ደረቅ ሆነ።

ሃፍረት የሌለው (እፍረት የሌለው) 1.(ስድብ) የማያፍር፥ ቅሌታም፥ ወራዳ፥ ነውረኛ። 2.ይሉኝታ የለሽ፥ የማይፈራ።

እፍረተ ስጋ ስ የሴት ወይም የወንድ ብልት።

እፍረተ ቢስ ቅ ሃፍረት የሌለው።

ታፈረ ግ ተፈራ፥ ተከበረ።

ተፋፈረ(ሩ) ግ ተፈራራ።

አሳፈረ ግ 1.አዋረደ፥ አቃለለ። 2.አስከበረ፥ አስጠበቀ።

አሳፋሪ ቅ አዋራጅ፥ ዝቅ የሚያደርግ፥ ቅሌት ላይ የሚጥል።

አፈር ስ 1.የተፈረፈረ ወይም የተቆፈረ የመሬት አካል። 2.አቧራ፥ ትቢያ።

አፈሩን ገለባ ያድርግለት የሞተን ሰው ስም በማንሳት ሃሳቡን ለመግለፅ የሚፈልግ ሰው የሟችን ስም ከመጥራቱ በፊት "መከራው ይቅለልለት" ለማለት የሚጠቀምበት የበጎ ምኞት መግለጫ ቃል።

አፈር ሆነ 1.ሞተ፥ ተቀበረ። 2.በሰበሰ፥ ወደአፈርነት ተለወጠ፥ ትቢያ ሆነ።

አፈር ስሆንልህ አንድ ነገር እንዲደረግ፥ እንዲሰራ ለመለመን የሚያገለግል የልምምጥ ወይም የማግባቢያ ቃል። *አፈር ስሆንልህ ይቺን ጉረስልኝ፡*

አፈር ለበሰ ተቀበረ።

አፈር አለበሰ ቀበረ።

አፈር አልባሽ 1.ቀባሪ (ዘመድ፥ ቤተሰብ፥ ወገን)። 2.ጧሪ ቀባሪ።

አፈር መለሰ ቀበረ፥ በአፈር ሸፈነ።

አፈረ መሰለ ፊቱ በጣም ጠቆረ፥ ጠወለገ፥ ተጎሳቆለ።

አፈር ቀመሰ 1.ሞተ። 2.ተቀበረ።

አፈር ቃመ 1.አፈር በላ። 2.በአፈር ተለወሰ፥ ተበላሸ።

አፈር በላ 1.ሞተ። 2.ተበላሸ፥ ከጥቅም ውጭ ሆነ።

አፈር በላው ሞተ።

አፈር ብላ/ቃም (እር.) ሙት፥ አፈር ሁን፥ ተቀበር።

አፈር ይብላኝ ሃዘንን ወይም መፀፀትን ለመግለፅ የሚያገለግል ቃል። *አፈር ይብላኝ ከቤቱ እንደወጣ በዚያው ድፍት ብሎ ቀረ።*

አፈር ጋጠ ብዙ ለፋ፥ ደከመ።

አፈር [ድቤ] አስጋጠ 1.በሃይል ደበደበ፥ መታ። 2.አለፋ፥ አደከመ።

አፈር ጠራው ከነበረበት ቦታ ወደ ሌላ ቦታ እንደ ሄደ በድንገት ሞቶ እዚያው ተቀበረ።

እንደ አፈር ነው ብዙ፥ ኣያሌ ነው።

አፈር ገፊ ስ ገበሬ፥ አርሶ አደር።

አፈርማ ቅ አፈር የሚመስል።

አፈርሳታ ስ አንድን ወንጀል በድብቅ የፈፀመን ሰው ለማውጣት ወይም ለማጋለጥ የሚደረግ የሰፈር ስብሰባ፣ አውጫጭኝ።

አፈሰ ግ 1.ዘገነ፥ ዛቀ፥ ተረፈሰ (እህልን፥ አፈርን፥ ...)። 2.ሰውን ያለፍላጎቱ በማስገደድ ወሰደ።

አፋሽ አጎንባሽ ማንኛውም ተራ ሰው፥ ትንሽ ትልቁ።

አፈሳ ስ 1.ለተወሰነ አላማ ሰዎችን ያለፍላጎታቸው ይዞ የመውሰድ ድርጊት። 2.ዝቅሽ፥ ርካሽ። *የዘንድሮው ገበያ አፈሳ ነው።*

ታፈሰ ግ 1. ተያዘ፥ ተወሰደ። 2. በብዛት ተገኘ፥ በረከተ (ምርት)።3. ተዛቀ፥ተተረፈሰ።

አፈቀላጤ "አፍ" ስር ተመ.

አፈተተ

እንደ አፈተተው እንደአሻው፡ እንደፈለገው። *እንደ አፈተተው ያድርግ*፡

አፈቸለ ግ ለፈለፈ።

አፈነ^{1} ግ 1.ትንፋሽ ከለከለ፥ ዘጋ። 2.አጨለመ፥ ሸፈነ (ጉም፥ ጭጋግ)። 3.ወሬን እንዳይሰራጭ ወይም እንዳይሰማ አደረገ። 4.የመናገር ወይም ሃሳብ የመግለፅ እድል አሳጣ። 5.በቤት አስሮ ቀለበ (እንስሳትን)። 6.አስገድዶ ወይም አንቆ ወሰደ። 7.አውድማ ላይ የሚያበራዩትን የበሬ አፍ አሰረ ወይም ሸበበ። 8.እጅብ እጅብ አደረገ፥ ከበበ።

ማፈኛ ስ የጆሮ ጌጥ፥ ጆሮ ላይ ከተሰካ በኋላ እንዳይወልቅ ከበስተኋላ በኩል ዘንጉ ላይ የሚሰካ ነገር።

አፈና ስ 1.አስገድዶ ወይም አፍኖ መውሰድ። 2.ጭጋግ፡ ጉምና ዝናብ የሆነበት ቀን።

አፋኝ [ቡድን] ስ ሰውን እያስገደደ የሚወስድ፥ የሚያስር፥ የሚሰውር ቡድን።

እፍንፍን ስ ትፍግፍግ፥ ጭንቅንቅ።

እፍንፍን አለ ግ ተጣበበ፥ ተጨናነቀ።

ታፈነ ግ 1.አየሩ በጢስ፡ በጭጋግ፥... ተበከለ፥ ተሞላ፡ ንፁህ አየር ታጣ። 2.ትንፋሹ ተቋረጠ፥ ተዘጋ።

ተፋፈነ ግ ተፋፈገ፥ እፍንፍን አለ።

አፈነ^{2} ግ በእፍኝ ዘገነ፥ ቆነጠረ።

እፍኝ ስ 1.ጥራጥሬ፥ ውሃ፥...መያዝ የሚያስችል የተገጣጠሙና ጣቶች ወደ ላይ ቀና ያሉበት የሁለት እጆች የውስጥ ክፍል። 2.በእፍኝ የተያዘ ወይም የተሰነ ጠጣር ወይም ፈሳሽ ነገር። 3.ጥርኝ፥ ጭብጥ።

አፈንገጠ "*ፈንገጠ" ስር ተመ.

አፈንጋጭ ዝ.ከ.

አፈና "አፈነ^{1}" ስር ተመ.

አፈኛ "አፍ" ስር ተመ.

አፈከፈከ ግ በህመም ምክንያት የሰውነት ቆዳ ሊገለፈፍ ወይም ሊቀረፍ ደረሰ፤ አሸቀሸቀ።

አፈገ ግ አመገ፥ አፈነ። 2-መሰገ፡ አከተ፡ አጎረ (ኩበትን)።

እፍግ ቅ በመተፋፈን ወይም በመታፈግ የሚፈጠር መጥፎ ሽታ፥ እምክ።

ታፈገ ግ ታመገ፤ ታመከ፤ ታፈነ።

ተፋፈገ ግ ተጣበበ፥ ተጨናነቀ።

አፈገፈገ ግ ወደ ኋላ ሸሸ።

አፈጠረ ግ (እስል.) የረመዳን ፆም ሲፆም ውሎ ማታ ላይ ምግብ በላ፥ ፈሰከ።

አፈጠፈጠ ግ አቆጠቆጠ፥ ቅጠል አወጣ።

አፈፈ ግ ከረከመ፡ አስተካከለ።

እፉፌ ቅ ቅራፊ፡ ቁራጭ።

***አፈፈ**

አፈፍ አለ ግ በፍጥነት ተነሳ፥ ብድግ አለ።

አፈፍ አፈፍ አለ ግ ፈጠን ፈጠን፥ ቸኮል ቸኮል ብሎ ተራመደ።

አፈፍ አደረገ ግ ለቀም አደረገ፥ በፍጥነት ያዘ ወይም ጨበጠ።

አፉ ስ እንደሰይፍ ያለ ትልቅ ቢላዋ፤ ካራ።

አፋኝ [ቡድን] "አፈነ^{1}" ስር ተመ.

አፋዊ "አፍ" ስር ተመ.

አፋፍ ስ 1.የገደል አፍ ወይም ጠርዝ። 2.የተራራ ወይም የከረብታ ጫፍ።

አፍ ስ 1.በውስጡ ምላስንና ጥርስን የያዘና ለምግብ መብያ፥ ለመተንፈሻና ለመናገሪያ የሚያገለግል፥ የሚዘጋና የሚከፈት የሰውነት ክፍል። 2.ስለት። *ሁለት አፍ ያለው ሰይፍ*። 3.ቋንቋ፥ ልሳን። *የፈረንጅ አፍ ያውቃል*። 4.ለማስገቢያና ለማስወጫ የሚያገለግል በአንድ በኩል ብቻ ያለ ክፍፍተት። *የጠርሙሱ አፍ ጠባብ ነው*። 5.ፊርጅ፥ ጠርዝ (የነጠላ፡ የጋቢ፡ ...)። *ሌላውን ቋጭቼ አንድ አፍ ይቀረኛል*። 6.(ዘይ.) ነገር፥ ጭቅጭቅ፥ ንትርክ። *አፍ ያበዛል*።



አፍ 1ኛ ፍቺ

ለአፉ ገደብ (ለከት) የለውም እንደልቡ፡ እንደመጣለት ይናገራል።

በአፈ በጠበቃዬ።

በአፍ በአፉ አጎረሰው በላይ በላዩ ቶሉ ቶሉ አጎረሰው።

አፉ ተዘጋ ዝም አለ።

አፉ ላይ ተንቀዋለለ የምግብ ፍላጎት ከማጣት የተነሳ የጎረሰው ምግብ አልዋጥ አለው።

'አፉን ለጎመ ዝም ወይም ፀጥ አለ፡ አልናገር አለ።

አፉን ሞልቶ ተናገረ በድፍረት፡ በሙሉ እምነት፥ ሳያመነታ፡ ሳይጠራጠር ተናገረ።

አፉን ነጠቅ ነጠቅ ያደርገዋል 1.ሲናገር እንደበቱ በጣም ይፈጥናል። 2.ሲናገር ጠንቃቃ አይደለም፤ መናገር የማይገባውን ሁሉ ይናገራል።

አፉን ነጠበው ሳያስበው፥ መናገር የማይገባውን ነገር በድንገት ተናገረ።

አፉን አሟሸ እህል ውሃ ቀመሰ።

አፍ ማሟሻ ስ ቁርስ።

አፉን አሾለ ለነገር፥ ለስድብ አቆበቆበ።

አፉን አበላሸ /አጠፋ የለመነውን ወይም የጠየቀውን ሳያገኝ ቀረ።

አፉን አዳለጠው /አዳጠው መናገር የማይገባውን ነገር ተሳስቶ ተናገረ፤ ነገር አመለጠው።

አፉን ከፈተ 1.ጮሀ፡ ቀባጠረ፤ ለፈለፈ። 2.በጣም ተስነነቀ።

አፉን ያዘ ዝም ወይም ፀጥ አለ።

አፉን አስያዘው ዝም ወይም ፀጥ አሰኘው፤ አሳፈረው።

አፉን ይበላዋል ለመናገር ይቸኩላል፡ ዝም ማለት አይችልም፤ እንዲናገር የሚገፋፋው ስሜት አለ።

አፉን ይይዘዋል በትክክል መናገር ይሳነዋል፤ ይንተባተባል፡ ይኮላተፋል (ለትልቅ ሰው)።

አፉን ጠበቀ የማይገባ ነገር እንዳይናገር ጥንቃቄ አደረገ።

አፉን ፈታ መናገር ጀመረ (ህፃን)።

አፈ ላይ ነው ትውስታው አእምሮዬ ውስጥ አያለ በአንደበቴ ነገሩን መጥራት አቃተኝ።

አፍ ለቀቀበት "ላሰ" ስር **"ምላስ ለቀቀበት"**ን ተመ.

አፍ ለአፍ ፊት ለፊት፥ ትይዩ።

አፍ ለአፍ ገጥመው ሲያወሩ ተቀራርበው በሹክሹክታ ሲያወሩ።

አፍ ቂጡ ሳቀ (ተራ.አነ.) በጣም ተደሰተ፥ ተፍነከነከ።

አፍ ቂጡ ሸበተ (ተራ.አነ.) በጣም አረጀ፥ አፈጀ።

አፍ ተካፈተ ተሰዳደበ፤ ክፉና ደግ ተነጋገረ።

አፍ አትስጠው አትመልስለት፥ አታናግረው።

አፍ አወጣ ተናገረ፤ ለፍላፊ ሆነ።

አፍ ያለው አስመስሎ መናገር የሚችል፡ ነገር አሳማሪ።

የአፍሽ የቂጥሽ ወሬ (ተራ.አነ.) ዝሙት ነክ ወሬ።

የአፍ አመል አለበት 1.ይዋሻል። 2.ወሬ ያሰብቃል ወይም ያመላልሳል።

አፈ ልስልስ መጥፎ ወይም ክፉ ነገር የማይናገር።

አፈ ምላጭ "ላጨ" ስር **"ምላጭ አፍ"**ን ተመ.

አፈ ሾሌ ቅ ከንፈሩ የበሰለ ሾላ የሚመስል (ፈረስ)።

አፈ ቀላጤ ስ 1.አንድን ሰው ወይም ቡድን ወይም ድርጅት ወክሎ መግለጫ የሚሰጥ ሰው። 2.ለአንድ ሰው ወይም ቡድን ወይም ድርጅት ወግኖ የሚከራከር።

አፈ ቅቤ /ጮማ ነገር አሳማሪ፤ አለስልሶና አሳምሮ የመናገር ችሎታ ያለው።

አፈ ቅይድ /እስር ኮልታፋ፥ ተብታባ፡ ለፍዳዳ።

አፈ ብልጥ 1.ጮሌ፡ ንግግር አሳማሪ። 2.በአነጋገሩ ጮሌ ወይም ብልጥ የሚመስልና በተግባር ሲታይ ግን ያልሆነ።

አፈ ታሪክ ስ በፅሁፍ ሳይሆን በቃል ብቻ ሲወርድ ሲዋረድ፡ ሲነገር የቆየ ታሪክ።

አፈ ንጉስ ስ 1.በንጉስ ቦታ ሆኖ ማንኛውንም ነገር የሚፈፅም የንጉስ ባለሟል። 2.የዳኞች የበላይ ሹም፤ አለቃ።

አፈ ለቃቃ ቅ ሰፊ አፍ ያለው (እቃ)።

አፈ ወረሳ ቅ አፉ እንዳመጣለት የሚቀባጥር፡ የሚያወራ።

አፈ ዋሾ ውሸታም፡ ሃሰተኛ።

አፈ ዘርጣ /ግም አፉ እንዳመጣለት የሚቀባጥር፥ አስተውሎ የማይናገር።

አፈ ዝናም ንግግር ከጀመረ የማያቋርጥ ወይም ብዙ የሚናገር።

አፈ ድስት ስ ከሆዱ ዘርጠጥ፥ ከአፉ ጠበብ ብሎ ከንፈሩ እንደ ድስት ወደውጪ ቀልበስ ያለ ብርሌ(ስእሉን ብርሌ ስር ተመ.)።

አፈ ጉባኤ ስ ጉባኤውን ወክሎ የሚናገር የጉባኤ አለቃ፥ ተጠሪ፥ መሪ።

አፈ ጨዋ 1.እውነትነት የሌለው፡ ያለአዋቂ ሰው የሚናገረው ወግ፥ ታሪክ። 2.መጥፎ ነገር የማይናገር።

አፈ ጭቃ አነጋገረ ጅል።

አፈ ፀያፍ መጥፎ፥ ነውር፥ ባለጌ ነገር የሚናገር።

አፈ ፃድቅ እውነተኛ ወይም ጥሩ ሰው በመምሰል በአፉ ጥሩ ነገር እየተናገረ መጥፎ ነገር የሚፈፅም።

አፍ ሳቻ ሳይታሰብ የተነገረ የአፍ ስህተት።

አፍ ተጅ ቅርብ፥ አጠገብ።

አፍ እላፊ ሊያስቀይም ወይም ሊያስቆጣ የሚችልና ተገቢ ያልሆነ ንግግር።

የአፍ ወለምታ ሌላውን የሚያስቀይም ወይም የሚያስከፋ ፀያፍ ንግግር።

አፈኛ ቅ ነገረኛ፥ ምላሰኛ፥ ለፍላፊ።

አፋዊ ቅ 1.በቃል ብቻ የሚነገርና በፅሁፍ የሌለ። 2.ከልብ፥ ከአንጀት ያልሆነ፤ ከአንገት በላይ የሆነ። 3.ውጫዊ፤ የላይን ቅርፅ ብቻ የሚያመለክት።

አፍለኛ "አፈለ" ስር ተመ.

አፍለኝ ዝ.ክ.

አፍላ ዝ.ክ.

አፍላል ስ ከማሰሮ የሚበልጥና ከእንስራ የሚያንስ ትልቅ ድስት።

አፍርንጅ ስ ለጥሬ ስጋ መብያ የሚያገለግል የተደቆሰና የተቀመመ የበርበሬ ፍሬ።

አፍሮ አይገባ ስ እንደ ጥንብ አንሳ ያለ ሆኖ ግን መጠኑ ከጥንብ አንሳ አነስ የሚል የአሞራ አይነት (ካልቀረቡት የማይሸሽ)።

አፍታ ተው.ግ. አጭር ጊዜ።

አፍን ስ ነብርማ መልክ ያለውና እንደ በግ፥ ፍየል፥... ያሉትን የሚበላ የዱር አውሬ።

አፍንጫ ስ ከአፍ በላይ ከግንባር በታች የሚገኝ፥ ለማሽተቻና ለመተንፈሻ የሚያገለግሉ ሁለት ቀዳዳዎች ያሉት የሰውነት ክፍል(በእሉን ራስ ስር ተመ.)።

አፍንጮ አፍንጫው ትልቅ ወይም ትንሽ ወይም ጎራዳ ወይም ደፍጣጣ የሆነ ሰው (በቀልድ የሚነገር)።

አፍንጫውን ነፋ ተቆጣ፥ አኩረፈ።

አፍንጫውን ይዞ ተቀበለው አስገድዶ፥ አስጨንቆ ተቀበለው።

አፍንጫ ጎራዳ ቅ አፍንጫው ትንሽና አጭር የሆነ፤ ቆንጋ።

አፎቄ ስ ትልቅ ስለታም ጦር።

አፎት ስ የሰይፍ ወይም የጎራዴ ቤት፤ ሰገባ።

ኤ የ **"እ"** ፊደል ሃምስ ዘር።

ኤሊ ስ ገላዋ በጣም ጠንካራ በሆነ ቅርፊት መሰል አካል (ዛጎል) የተሸፈነና አረማመዷ በጣም ዝግ ያለ፥ አስፈሪ ነገር ስታይ ጭንቅላቷንና እግሮቿን ከጠንካራው ሽፋኗ ውስጥ የምትደብቅ እንስሳ።



ኤሊ

ኤሌክትሪክ ስ ሙቀትን፥ ብርሃንን የሚሰጥ እንዲሁም ማሽኖችን ለማንቀሳቀስ የሚያስችል ኤሌክትሮንና ፕሮቶን ከተባሉ ነገሮች በተለያየ መንገድ የሚገኝ ሃይል።

ኤሌክትሪክ ማሞቂያ ስ በቅዝቃዜ ጊዜ አንድን ክፍል በኤሌክትሪክ ሃይል ለማሞቅ የሚያገለግል መሳሪያ።

ኤሌክትሪክ ሽቦ ስ ለኤሌክትሪክ ማስተላለፊያ ተብሎ የተሰራ የመዳብ ሽቦ።

ኤሌክትሪክ ገመድ ስ የኤሌክትሪክ ሃይል በውስጡ ለማስተላለፍ የሚችል የፕላስቲክ ሽፋን ያለው ሽቦ።

ኤሌክትሪክ ጋን ስ የኤሌክትሪክ ሃይልን ከጣቢያው ተቀብሎ በተፈለገው መጠን (ጉልበት በመጨመር ወይም በመቀነስ) ለተጠቃሚው አካባቢ የሚያሰራጭ ትልቅ የኤሌክትሪክ እቃ፤ ትራንስፎርመር።

የኤሌክትሪክ ሃይል ስ የኤሌክትሪክ ጉልበት፤ የመብራት ሃይል።

የኤሌክትሪክ መስመር ስ የኤሌክትሪክ ሃይል የሚተላለፍበት ሽቦ።

የኤሌክትሪክ ምድጃ ስ በኤሌክትሪክ የሚሰራ ምድጃ።

የኤሌክትሪክ ጉልበት ስ የኤሌክትሪክ ሃይል።

ኤምባሲ ስ የአንድ አገር አምባሳደር ተልእኮና ተግባር የሚከናወንበት መስሪያ ቤት።

ኤሮግራም ስ ተጣጥፎ እንደ ፖስታ ሊታሸግ የሚችልና ሌላ ፖስታ እንዲሁም ቴምብር የማያስፈልገው በአየር የሚላክ የደብዳቤ መጻፊያ ወረቀት።

ኤንቬሎፕ ስ ደብዳቤ አሽጎ ለመላክ የሚያገለግል የወረቀት ከረጢት፤ ፖስታ። አልፎ አልፎ አምቦልክም ይባላል።

ኤክስሬይ ስ በአጭር ርቀት ወደ አንድ አካል ውስጥ ዘልቆ በመግባት ተፈላጊውን የሰውነት ወይም የአካል ክፍል ለማሳየትና በፊልም ለመቅረፅ የሚያስችል ሃይለኛ የብርሃን ጨረር። አልፎ አልፎ ፊልሙም ሆነ መሳሪያው ኤክስሬይ ይባላል።

ኤክስሬይ አነበበ ኤክስሬዩ (ፊልሙ) ላይ የተነሳውን ወይም የተቀረፀውን ምስል በማየት ምን እንደሆነ ተናገረ፥ ተረጎመ።

ኤክስፐርት ስ በአንድ የሙያ መስክ የተለየና ጠለቅ ያለ እውቀት ያለው ባለሙያ።

ኤዲተር ስ አርታኢ።

ኤዲያ ቃ.አ. 1.ወዲያ! ኢጭ! ለማስትና ፐሳቻን፥ ንቀትን፥... ለመግለፅ የሚያገለግል ቃል። ***ኤዲያ! አትጨቅጭቂኝ***፡ 2.አንድን ነገር

በማጋነን ለማድነቅ የሚነገር ቃል:: *ሌፈያ/እንዲህ ነው እንጂ ስራ::*

ኤድስ ስ በሽታን የመቋቋም ተፈጥሮአዊ ሃይልን በማዳከም ሰውነት በቀላሉ በበሽታ እንዲጠቃና ለሞት እንዲበቃ የሚያደርግ፡ ብዙውን ጊዜ በግብረ ስጋ ግንኙነት እማካኝነት በሚተላለፍ ቫይረስ የሚመጣ በሽታ::

ኤግዚቢሽን ስ 1. የስእል፡ የምርት ውጤቶች፣...ትርኢት:: 2. ህዝብ እንዲያያቸው የተፈለጉ ነገሮች ተሰብስበው የሚታዩበት ቦታ ወይም አዳራሽ፤ መካነ ትርኢት::

ኤጲስ ቆጶስ ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ማእረጉ ከቀሞስ በላይ+ ከጳጳስ በታች የሆነ መንፈሳዊ አባት::

እ የ "**አ**" ፊደል ሳድስ ዘር::

እ— ሃላፊ ካልሆነ ግስ ጋር እየተጣመረ የሚገባ የአንደኛ መደብ አመልካች ምእላድ:: *እመጣለሁ::*

እሁድ ስ በቅዳሜና በሰኞ መካከል ያለው ቀን ስም፤ የሳምንቱ መጀመሪያ ቀን::

እህ

እህ አለ ግ ወሬ ጠየቀ፣ ሰበሰበ፣ አዳመጠ::

እህህ የሃዘን፣ የህመም ስሜት የሚገለፅበት ድምፅ::

እህል ስ 1.ለምግብ የሚያገለግል የአዝርእት ውጤት:: 2.ምግብ::

እህል ቀመሰ ተመገበ፣ በጥቂቱ በላ::

እህል በእህል ማባያው ስጋ የሌለበት ምግብ::

እህል ውሃ 1.አንዱ ከሌላው ጋር በመኖር የሚያሳልፈው ጊዜ:: 2. እድል ወይም እጣ ፈንታ:: *እህል ውሃዬ ሆኖ እዚሁ ቤት ላረጅሁ::* 3.ኑሮ፣ ህይወት:: 4.ምግብና መጠጥ::

እህል ውሃ አያሰኝም ትልቅ ወይም ከባድ ነው፤ ቢመጣ ሊገድል ይችላል:: *ቶሎም እህል ውሃ ሊያሰኝም::*

እህል ውሃው አለቀ ካለበት ቦታ ለቀቀ፤ ሞተ፤ ተለያየ (አብሮት ከነበረው ሰው ጋር)::

እህት ስ 1.ከአንድ እናትና አባት ወይም ከሁለቱ በአንደኛው ከተወለዱት ልጆች መካከል ሴቷ ልጅ ለወንዱ ልጅ ወይም ለሌላይቱ ሴት ልጅ ያላት የስጋ ዝምድና መጠሪያ:: 2.ባላት ቀረቤታ (በዝምድና፣ በቤተሰብነት) እንደ እህት የምትቆጠር የሴት ዘመድ:: 3. የማያውቋትን ሴት በትህትና ለመጥራትና ለማናገር የሚያገለግል ቃል::

እህትማማች (እትማማች) ስ ከአንድ እናትና አባት ወይም ከሁለቱ በአንዱ የተወለዱ ሴት ልጆች::

እለት ስ ቀንና ሌሊትን ጨምሮ ያለው ሃያ አራት ሰአት፤ ቀን::

የእለቱ እለት (የለቱለት) በዚያኑ ቀን፣ በዚያው እለት::

የእለት እራት/እንጀራ ስ የእለት ምግብ::

እላቂ "አለቀ" ስር ተመ.

እላፊ "አለፈ" ስር ተመ.

እሌት ስ ዱቄት ከተነፋ በሃላ በወንፊት ላይ የሚቀረው ቅጥቃጭ፣ ንፋሽ፣ ጥራጊ ዱቄት::

እልህ (እልክ) ስ እንዴት ተደፈርኩ፣ ተነካሁ የሚያሰኝ የእምቢታ፣ የሞገደኛነት ስሜት::

እልህ አስጨራሽ እጅግ በጣም አድካሚ፣ አስቸጋሪ፣ አሰልቺ::

እልህ ያዘው የእልህ ስሜት አደረበት::

እልሀኛ (እልከኛ) ቅ የእልህ ስሜት ያለበት፤ ሞገደኛ::

እልል

እልል (እልልታ) ስ እልል እልል በማለት የሚገለፅ የደስታ ጩሀት::

እልል አለ ግ 1.እልልታ አሰማ:: 2.ተደሰተ::

እልም¹

እልም እልም አለ ግ በጣም በጥቂቱ፣ በትንሹ ተሰማ (ለማጣፈጫ የሚጨመር ጨው፣ ስኳር፣...):: *ጨው ሊታወቅ እልም እልም ካለ ይበቃል::*

እልም² "**ህልም**"ን ተመ.

እልም

እልም አለ ግ 1.ጠፋ፣ ጨለመ (መብራት):: 2.ጠፋ፣ አልገኝ አለ፣ ትዝ አልል አለ:: 3.ጠፋ፣ ተሰወረ:: 4.ተደመሰሰ (ፅሁፍ):: 5.ሄደ፣ ነጎደ::

እልም ድርግም አለ ግ ፈፅሞ ጠፋ::

እልምልም አለ ግ 1.ጠፋ፣ ጭልምልም አለ (መብራት):: 2.ተበላሸ፣ ተደመሰሰ፣ ወደመ::

እልምልም አደረገ ግ 1.አጠፋ፣ አጨለመ (መብራትን):: 2.አበላሸ፣ አወደመ፣ ደመሰሰ:: 3.አባከነ፣ አጠፋ (ገንዘብን፣...)::

እልቀት "አለቀ" ስር "**እልቂት**"ን ተመ.

እልቂት "አለቀ" ስር ተመ.

እልቅት ስ በአንገትና በደረት መጋጠሚያ ላይ ጎድጎድ ብላ የምትገኝ የሰውነት ክፍል(ሰእሉን ሰውነት ስር ተመ.)::

እልቅና "አለቃ" ስር ተመ.

እልቆ መሳፍርት "ሁልቆ መሳፍርት"ን ተመ.

እልበት (ህልበት) ስ ጎንቀሉ የደረቀ አብሽ ከተከካ ባቄላ ጋር በማስፈጨት እንደ ገንፎ

ተዘጋጅቶ በደንብ ከቀዘቀዘ በሂላ በማንኪያ ወይም በእጅ እስኪቀጥን ድረስ ተመትቶ ብዙውን ጊዜ ከስኳር ጋር እየተቀላቀለ በእንጀራ የሚበላ የምግብ አይነት።

እልባት "**አለበ**^{2}" ስር ተመ.

እልከኛ "**እልሁ** ስር "**እልሀኛ**"ን ተመ.

እልክ "**እልህ**"ን ተመ.

እልፈት "**አለፈ**" ስር ተመ.

እልፈት ዝ.ከ.

እልፍ^{1} ስ 1.አስር ሺህ። 2.(ዘይ.) ብዙ፣ አያሌ።

አእላፍ ስ መቶ ሺህ።

እልፍ አእላፍ/አእላፋት ቅ እጅግ ብዙ፣ አያሌ።

እልፍ^{2} ስ የስንጌ ወይም የገብስ እሸት ዛላ፣ አንድ ራስ እሀል።

እልፍኝ ስ ቀደም ባለው ጊዜ ነገስታቱና መኳንንቱ ታላላቅ እንግዶችን ለመቀበያና ለማስተናገጃ ይገለገሉበት የነበረና ከዋናው ቤት በስተሂላ በኩል የሚገኝ ትንሽ ቤት።

እልፍኝ አስከልካይ ስ የእልፍኝ አሽከሮች አለቃ።

[የ]እልፍኝ አሽከር ስ 1.በቤተ መንግስት ውስጥ ያልተፈቀደለት ሰው ወደ ቤተ መንግስት እንዳይገባ የሚጠብቅ በእልፍኝ አስከልካይ የሚታዘዝ አሽከር። 2. ቀደም ባለው ስርአት የቤተ መንግስት አንጣፊ፣ ጋሪጅ፣ አሲታማቢ፣ አልባሽ የነበረ ሰራተኛ ይጠራበት የነበረ ስም።

እልፍ አእላፍ "**እልፍ**^{1}" ስር ተመ.

እመም^{1} "**ህመም**"ን ተመ.

እመም^{2} "**አመመ**^{2}" ስር ተመ.

እመምኔት "**ምኔት**" ስር ተመ.

እምር

እምርታ ስ 1.ዝላይ። 2.እድገት፣ እርምጃ።

እምር አለ (ምር አለ) ግ እንጣጥ ብሎ ተራመደ።

እምር እምር አለ ግ ፈጠን ፈጠን እያለ በረጅሙ ተራመደ።

እመበለት (መበለት) ስ 1.መነኩሲት። 2.ባሏ የሞተባት ወይም በብቸኝነት የምትኖር ጠና ያለች ሴት።

እመቤት ስ 1.ባለፀጋ ወይም ሃብታም ሴት። 2.ቆንጆ፣ ውብ፣ ደርባባ ሴት።3. ሃላፊ፣ አዛዥ፣ አስተዳዳሪ ሴት(በመኖሪያ ቤት)።

እመብርሃን ስ የቅድስት ድንግል ማርያም ሌላ መጠሪያ።

እመት^{1} **(እምነት)** ስ በውሃ በጥብጦ ቢጠጡት ወይም ሰውነትን ቢቀቡት ከህመም ይፈውሳል ተብሎ የሚታመንበት በቤተ ክርስቲያን የሚወሰ አጣን አመድ።

እመት^{2} ስ 1. ሴት ስትጣራ "አቤት፣ ምን ልታዘዝ..." ለማለት በስም የተጠራው ሰው ለጠራዋ የሚያሰማው የትህትና መልስ ። 2.ትልልቅ ሴቶችን እመቤቴ ወይም እሜቴ ለማለትና አክብሮትን ለመግለፅ ስምን ቀድሞ የሚገባ ቃል። *እመት እገሊት*፡

እመጫት ስ 1.ከወለደች ብዙ ያልቆየች ወይም አራስ ሴት። 2.ከዛፍ ላይ የሚበቅል የሌላ እፅዋት ችግኝ። 3.በፅሀፈት ወቅት ተዘልሎ የነበረና መፃፍ በነበረበት ቦታ ትክክል ወደላይ ከፍ ብሎ የሚፃፍ ወይም የሚገባ ቃል፣ ስርዋፅ።

እሙን "**አመነ**" ስር ተመ.

እማ "**እማ ማ**"ን ተመ.

እሚታ ስ ሴት አያት።

እማሆይ ስ የመነኩሲት መጠሪያ።

እማማ (እማ፣ እማዬ) ስ 1.ልጆች እናታቸውን የሚጠሩበት ቃል ወይም የተዘምዶ ስም። 2.በእድሜ የገፉች ታላቅ ሴትን በአክብሮት ለመጥራት ስምን ቀድሞ ወይም ብቻውን የሚነገር ቃል።

እማኝ ስ ምስክር።

እማኝ አነሳ ምስክር ቆጠረ ወይም ጠራ።

እማዬ "**እማማ**"ን ተመ.

እሜቴ ስ በእድሜም ሆነ በደረጃ ከፍ ብላ የምትገኝን ሴት በአክብሮት ለመጥራት የሚያገለግል ቃል።

እምር

እምር ታህል በጣም ትንሽ።

እምስ ስ (ነውር) የሴት ብልት ወይም ሃፍረተ ስጋ(በእሱን ሰውነት ስር ተመ.)።

እምስ አንቀጥቅጥ/ፈሬ ስ በአብዛኛው በገደል አካባቢ የሚበቅል አነስተኛ የእፅዋት አይነት።

እምስ "**አመሰ**" ስር ተመ.

እምቅ "**አመቀ**" ስ . ተመ.

እምቡር "**እንቡር**"ን ተመ.

እምቡሶ (እንቡሶ) ስ አብዛኛውን ጊዜ በወይና ደጋ የሚበቅል የእፅዋት አይነት።

እምቡሽቡሽ ስ ጉሽ ጠላ።

እምቡጣ "**እንቡጣ**"ን ተመ.

እምቡጣጢያ "**እንቡጣጥያ**"ን ተመ.

እምቡጥ "**እንቡጥ**"ን ተመ

እምቡፍና "**እንቡፍና**"ን ተመ.

እምቢ "**እንቢ**"ን ተመ.

እምቢልታ "እንቢልታ"ን ተመ.

እምባ "አነባ" ስር "እንባ"ን ተመ.

እምብርት "እንብርት"ን ተመ.

እምብርክክ "*በረከከ" ስር "እንብርክክ"ን ተመ.

እምብዛም (**እምብዛ**) አፍራሽ አንቀፆችን እያስከተለ ብዙም፥ እስከዚህም፥ ... የሚለውን አሉታዊ ስሜት ለመግለፅ የሚነገር ተውሳከ ግሳዊ ቃል ። *ወረቀቱ እምብዛም አይፈለገም/ እዚህ ሰፈር እምብዛም አይመጣም።*

እምቦሳ "እንቦሳ"ን ተመ.

እምቦጭ አለ "ነቦጨ" ስር ተመ.

እምቦፍ አለ "ቦፍ" ስር ተመ.

እምቧይ "እንቧይ"ን ተመ.

እምቧ "እንቧ"ን ተመ.

እምቧጮ "እንቧጮ"ን ተመ.

እምነት¹ "አመነ" ስር ተመ.

እምነት² "እመት¹"ን ተመ.

እረብ አለ "ረብ¹" ስር ተመ.

እረኛ ስ 1.ጠባቂ፥ አጋጅ (ከብትን)። 2.(በድብ፡ ዘይ.) ባለጌ፥ ስድ።

እረፍት "አረፈ" ስር ተመ.

እሩምታ ስ ለተወሰነ ጊዜ ያለማቋረጥ የሚሰማና ተከታታይነት ያለው የጥይት ተኩስ።

እሩር "ሩር"ን ተመ.

እሪ

እሪታ ስ አደጋ በደረሰ ጊዜ እርዳታ ለመጠየቅ የሚደረግ የጩሀት ማሰሚያ ቃል፤ ኡኡታ።

እሪ አለ ግ ለደረሰበት አደጋ እርዳታ ለማግኘት ጮሀ፤ ኡኡ አለ።

እሩሽ "አረሰ¹" ስር ተመ.

እሩት "ሩት"ን ተመ.

እሩቻ "ሩቻ"ን ተመ.

እሩፌ ስ የጨርቅ ቁራጭ።

እሬት "ሬት"ን ተመ.

እሬንሳ "ሬንሳ"ን ተመ.

እርማት "አረመ" ስር ተመ.

እርም ስ ክልክል፤ ውጉዝ፥ ሃራም። *የሰው ስጋ መብላት እርም ነው።*

እርሙን በላ ከነእርሙ በላ።

ከነእርሙ በላ የዘመዱን ሞት ሳይሰማ ቀረ ወይም እልቅሶ እርሙን ሳያወጣ ቀረ።

እርመ በላ ዘመዱ መሞቱን ሰምቶ ያላለቀሰ ወይም ለቅሶ ያልደረሰ።

እርሙን አወጣ 1.የዘመዱን ሞት ሰምቶ አለቀሰ። 2.አንድ ነገር ተመልሶ እንደማይመጣ፥ እንደማይደረግ፤... ወይም ይሆናል ብሎ ያሰበው ወይም የተመኘው ነገር እንደማይሆን በመረዳት ተስፋ ቆረጠ።

እርም ታህል በጣም ትንሽ።

እርም አለ ፈፅሞ ተው፥ አቋረጠ፥ አቆመ።

እርም ይሁንብኝ ድጋሚ አላደርገውም። *እርም ይሁንብኝ ሁለተኛ መጠጥ ላልጠጣም።*

እርምት "አረመ" ስር "እርማት"ን ተመ.

እርምጃ "*ረመደ" ስር ተመ.

እርምጥምጥ "ረመጠ" ስር ተመ.

እርርት ስ 1.በሰውና በከብት አይን ላይ የሚወጣ ሞራ መሳይ ነገር። 2.በከብት ጭራ ላይ የሚወጣ ቁስል።

እርሳዎ ተው.ስ. በሁለተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር የሚነገር ተባእታይም ሆነ አንስታይ ያታን በአክብሮት ለመጥራት የሚያገለግል ተውሳጠ ስም።

እርሱ "እሱ"ን ተመ.

እርሳስ "ረሰሰ" ስር ተመ.

እርሳቸው "እሳቸው"ን ተመ.

እርሷ "እሷ"ን ተመ.

እርሻ "አረሰ¹" ስር ተመ.

እርሾ ስ 1.ያልቦካን ሊጥ እንዲቦካ የሚያደርግ ቀደም ብሎ የቦካ ሊጥ፤ የሰነበተ የሊጥ ቅሪት። 2.ባይካርቦኔት ሶዳ የሚባልና ሊጥ እንዲቦካ የሚያደርግ፥ በዱቄት መልክ የተዘጋጀ ኬሚካል። 3.አንድን ተግባር ለማከናወን እንደመነሻ ሆኖ የሚያገለግል መጠነኛ ገንዘብ ወይም ጥሪት።

እርቃን ስ ራቁት፥ መለመላ።

እርቃኑን ቀረ 1.ራቁቱን ሆነ። 2.አጣ፥ ደሀየ። 3.ተጋለጠ፥ መጥፎ ስራው ታወቀ።

እርቃኑን አስቀረው 1.ያለውን ሁሉ ወሰደበት፤ ሰረቀው። 2.ራቁቱን አስቀረው። 3.አጋለጠው።

እርቃን ስጋ ስ ያልለበሰ ወይም ራቁቱን የሆነ አካል፤ ሰውነት።

እርቅ "*አረቀ" ስር ተመ.

እርባታ "ረባ" ስር ተመ.

እርባና ቢስ ዝ.ክ.

እርባን¹ ስ የተለያየ ጥቃቅን ቅርፃ ቅርፅ ያለበትና በረቀቀ ዘዴ በጥበብ የተሰራ የቀለበት፥ የከርቻ፥ የመስቀል፤ ... ንቅስ ወይም ንድፍ።

እርባን ስራ ስ በሳጹ ቀጭን ሽቦ የተጠመጠመበትና ረቂቅ ንቅስ ያለበት፡ የረቀቀ አሰራርን የተከተለና ውበት ያለው የወርቅ ወይም የብር ጌጥ ስራ።

እርባን^2 **"ረባ"** ስር **"እርባና"**ን ተመ.

እርብትብት **"*ረበተበተ"** ስር ተመ.

እርብድብድ **"*ረበደበደ"** ስር ተመ.

እርቦ ስ 1.የቁና አንድ አራተኛ የሆነ የእህል መስፈሪያ። 2.ከስፌት የተሰራ የቁርስ ወይም የቆሎ ማቅረቢያ። 3.ጢሰኛ ለባለርስት ይሰጠው የነበረ አንድ አራተኛ የምርት ውጤት።

እርቦ አራሽ ስ የባለርስትን መሬት እያረሰ ከሚያገኘው ምርት አንድ አራተኛውን ለባለርስቱ የሚሰጥ ገበሬ።

እርቦ አፍሳሽ ዝ.ከ.

እርከን ስ 1.ደረጃ፤ መውጫ መውረጃ። 2.መሬት እንዳይሸረሸርና በጎርፍ እየተጠረገ እንዳይወሰድ ደግፎ የሚይዝ የድንጋይ ካብ። 3.ለመንግስት ሰራተኛ በየተወሰነ ጊዜ የሚሰጥ የደመወዝ ጭማሪ።

እርኩም ስ ሙሉ በሙሉ ጥቁር ሆኖ ከፊቱ በኩል አንገቱ አካባቢ ቀይ ያለበትና መንቁረ ረዥም የሆነ ከጥንብ አንሳ ከፍ የሚል ትልቅ የአሞራ አይነት።

እርኩም አፍ (ስድብ) ያሞጠሞጠ ወይም የሾለ አፍ ያለው።

እርኩስ **"ረከሰ"** ስር ተመ.

እርካብ **"ርካብ"**ን ተመ.

እርካታ **"ረካ"** ስር ተመ.

እርክፍካፎ **"*ረከፈከፈ"** ስር ተመ.

እርኮት ስ ከበሬ ወይም ከጉማሬ፥... ቆዳ የሚሰራ የውሃ መያዣ።

እርዛት **"*አረዘ"** ስር ተመ.

እርዳታ **"ረዳ"** ስር ተመ.

እርድ^1 ስ ቢጫ ቀለም ያለው የቅመም አይነት።

እርድ^2 **"አረደ"** ስር ተመ.

እርጅና **"አረጀ"** ስር ተመ.

እርገት **"አረገ"** ስር ተመ.

እርጉም **"ረገመ"** ስር ተመ.

እርጉዝ **"*ረገዘ"** ስር ተመ.

እርጋታ **"ረጋ"** ስር ተመ.

እርጋጭ **"ረገጠ"** ስር ተመ.

እርግማን **"ረገመ"** ስር ተመ.

እርግብ **"ርግብ"**ን ተመ.

እርግብግቢት **"*ረገበ"** ስር ተመ.

እርግብግብ ዝ.ከ.

እርግዝና **"*ረገዘ"** ስር ተመ.

እርግጠኛ **"*ረገጠ"** ስር ተመ.

እርግጥ ዝ.ከ.

እርግጫ **"ረገጠ"** ስር ተመ.

እርግፍግፍ አለ **"*ረገፈገፈ"** ስር ተመ.

እርኅ **"ረጋ"** ስር ተመ.

እርኳ ስ መጠርጠሪያ ውስጥ በሚጋደም ቀሰም ውስጥ ተሰክታ፥ ቀሰሙ (ድውሩ) እንዲሽከረከርና ማጉ በድሩ መካከል እንዲዘረጋ የምትረዳ እንደሰንበሌጥ አገዳ ያላት ቀጭን ሽመል።

እርጥባን **"ረጠበ^2"** ስር ተመ.

እርጥብ **"ረጠበ^1"** ስር ተመ.

እርጥጥ **"ረጠጠ"** ስር ተመ.

እርጭ

እርጭ (ረጭ) አለ ግ ፀጥ፡ ዝም አለ።

እርፈት **"አረፈ"** ስር **"እረፍት"**ን ተመ.

እርፍ ስ በአንድ በኩል ከማረሻና ከሞፈር ጋር የሚቀደድ፥ በሌላ በኩል ገበሬ ሲያርስ የሚጨብጠውና የማረሻውን ጥልቀትና ሂደት የሚቆጣጠርበት የበሬ እቃ(ስእሉን ሞፈር ስር ተመ.)።

እርፈ መስቀል ስ ከመያዣው በኩል የመስቀል ቅርፅ ያለበት የስጋ ወደሙ ማቀበያ ወይም መስጫ ማንኪያ።

እርፍ መጣያ ስ ገበሬ የእርሻ ስራውን በነሃሴ ወር ከጨረሰ በሂላ የግብርና እቃውን የሚያስቀምጥበት ወቅት።

እሮሮ **"ሮሮ"**ን ተመ.

እሰይ ደግ፥ ማለፊያ ለማለት የሚነገር የደስታ መግለጫ ቃል።

እሱ (እርሱ) ሶስተኛ መደብ ተባእታይ ፆታ፥ ነጠላ ቁጥርን የሚያመለክት ተውላጠ ስም።

እሳቤ **"አሰበ"** ስር ተመ.

እሳት ስ 1.ብርሃንና ሙቀት የሚሰጥና የማቃጠል፥የማፍላት፥የማብሰል፥ የማንደድ፥... ሃይል ያለው ነዲድ ወይም ፍም። 2.(ዘይ.) ጎበዝ፥ ቀልጣፋ፥ ንቁ፥ ጮሌ። *በትምህርቱ እሳት ነው።*

እሳት ሆነ 1.በጣም ተናደደ፥ በሸቀ። 2.እጅግ ተወደደ፥ ውድ ሆነ። *ቡና ባሁኑ ጊዜ እሳት ሆኗል።*

እሳት መታው በእሳት በጣም በሰለ።

እሳት ሰደደበት ቃጠሎ አስነሳ፥ በእሳት አያያዘ፥ ለኮሰ።

እሳት በላው እሳት ፈጀው፥ አቃጠለው።

እሳት ተነሳ የእሳት ቃጠሎ ወይም አደጋ ተፈጠረ።

እሳት አፍ (ስድብ) ለፍላፊ፣ ነገረኛ፣ ምላሰኛ።

እሳት ገባው ከሚያስፈልገው በላይ በሰለ።

እሳትና ጭድ የማይስማሙ፣ አጥፊና ጠፊ።

እሳተ ገሞራ ስ ከመሬት ከርስ ውስጥ የቀለጠ ድንጋይና ሌሎች ነገሮችን በመያዝ ፈንድቶ የሚወጣ እሳት።

እሳት አደጋ ስ 1.በእሳት ምክንያት በቤት ወይም በንብረት ላይ የሚደርስ አደጋ፣ ቃጠሎ። 2.በእሳት ምክንያት በቤት ወይም በንብረት ላይ ቃጠሎ ሲነሳ ጥሪ እየተደረገለት አደጋውን የሚከላከል ድርጅት(ሙሉ መጠሪያው የእሳት አደጋ መከላከያ ነው መኪናውም እሳት አደጋ ይባላል) ።

የእሳት ላንቃ ስ የእሳት ነበልባል።

የእሳት ራት ስ ማታ ማታ በእሳት ወይም በመብራት ዙሪያ የምትበር ቢራቢሮ።

የእሳት ራት

የእሳት ክፋይ ና ጫቀ በእሳት የፋመ የእንጨት ጉማጅ።

እሳቸው (እርሳቸው) እሱ ወይም እሷ በሚባሉት ተውላጠ ስሞች ፈንታ የሚገባ የአክብሮት ተውላጠ ስም።

እስላም "ሰለመ" ስር ተመ.

እስልምና ዝ.ከ.

እስረኛ "አሰረ" ስር ተመ.

እስራት ዝ.ከ.

እስር ዝ.ከ.

እስስት[1] ስ 1.የመልኳን ቀለም ከአካባቢዋ ቀለም ጋር የምታመሳስል፣ዝርያዋ ከገበሎ ወገን የሆነ፣ረዥም ምላስ ያላት አነስተኛ ፍጡር። 2.(ዘይ.) ባህሪው የሚለዋወጥ፣ ጠባዩ የማይታወቅ ሰው።

አስስት 1ኛ ፍቺ

እስስት[2] ስ ማንቁርት። *እስስቱን ለንቶ ገንዘቡን ተቀበለው።*

እስቱኮ "ስቱኮ"ን ተመ.

እስቲ "እስኪ" ን ተመ.

እስታዲየም "ስታድየም"ን ተመ.

እስቴንስል "ስቴንስል"ን ተመ.

እስቴፕለር "ስቴፕለር"ን ተመ.

እስትንፋስ ስ ትንፋሽ።

እስትንፋስ ዘራበት ህይወት ሰጠው።

እስከ መዋ. መድረሻን አመልካች ቃል። *እስከ ድሬዳዋ እሄዳለሁ/ እስከ ነገ እቆያለሁ።*

እስኩታ ስ በጠላ ላይ የሚንሳፈፍ የጌሾ፣ የብቅልና የአሻሮ አሰር፣ ገፈት።

እስኪ(እስቲ) (አንድን ድርጊት)ፈፅም/አትፈፅም፣ አድርግ/አታድርግ ለማለት ከግስ ቀድሞ የሚነገር ቃል። *እስኪ ሂሬው/ እስኪ ስጠኝ/ እስኪ ንካኝ።*

እስክሪቢቶ "ስክሪቢቶ"ን ተመ.

እስክስታ (እስክስ) ስ በዘፈን ጊዜ ምትን ጠብቆ የሚደረግ የትከሻና የአንገት እንቅስቃሴ።

እስክስታ ወረደ (እስክስ አለ) በዘፈን ጊዜ ምትን ጠብቆ በትከሻና በአንገቱ እንቅስቃሴ አደረገ።

እስኮላርሽፕ "ስኮላርሽፕ"ን ተመ.

እስኮችቴፕ "ስኮችቴፕ"ን ተመ.

እስኳድራ"ብረት" ስር "ብረት ማእዘን"ን ተመ.

እስፒል "ስፒል"ን ተመ.

እሷ (እርሷ) በሶስተኛ መደብ ነጠላ ቁጥር፣ እንስታይ ፃታን የሚያመለክት ተውላጠ ስም።

እሸት "ሸተ" ስር ተመ.

እሺ 1. ለአንድ ድርጊት፣ ስራ፣... መስማማትን፣ ፈቃደኛነትን ለመግለፅ የሚባል ቃል።2. በጋራ ጨዋታ ወይም ንግግር ጊዜ አድማጭ አውራውን ቀጥል፣ ከዚያስ፣... ለማለት የሚጠቀምበት የወሬ ማራዘሚያ ቃል።

እሺታ ስ ፈቃደኛነት፣ መስማማት፣ ይሁንታ።

እሺ አለ ግ ተስማማ፣ ፈቃደኛ ሆነ።

እሺ ባይ ቅ ታዛዥ፣ ይሁን ባይ።

እሽ 1.ዝንብን፣ ወፍን፣ ዶሮን ለማባረር የሚነገር ቃል። 2.ዝም በል ወይም ፀጥ በል ለማለት የሚነገር ቃል።

እሽ አለ ግ 1.ዝንብን፣ ወፍን፣ ዶሮን አባረረ፣ ተከላከለ። 2.ዝም በል ወይም ፀጥ በል አለ።

እሽል "አሸለ" ስር ተመ.

እሽም "አሸመ" ስር ተመ.

እሹሩሩ የታዘለ ወይም በእቅፍ የተያዘ ህፃን ሲያለቅስ ዝም እንዲል እየተወዛወዙ በዜማ የሚባል የማባበያ ቃል።

እሹሩሩ አለ ግ 1.የሚያለቅስ ህፃን ልጅ ዝም እንዲል በዜማ እሹሩሩ እያለ አባበለ፤ ዝም እንዲል አደረገ። 2.(ዘይ.)ተለማመጠ፣ አሽበለበለ።

እሽቅድድም (እሽቅድምድም) "ቀደመ" ስር ተመ.

እሽኮለሌ ስ የስድብ ምልልስ።

እሽኮኮ "እንኮኮ"ን ተመ.

እሽግ "አሸገ" ስር ተመ.

እሾህ (እሾክ፤ ሾክ) ስ እንደ ኢጋም፤ግራር፣ ... ባሉ እፅዋት ላይ የሚገኝ እንደመርፌ ሹል የሆነና የሚዋጋ የእፅዋት አካል።

እሾህ ነው ክፉ፣ ነገረኛ ነው።

እሾህ አፍ ቅ (ስድብ) ተሳዳቢ፣ ነገረኛ (ሰው)።

እቁባት "ቁባት"ን ተመ.

እቁብ ስ 1.ሰዎች በተወሰነ ጊዜ የተወሰነ ክፍያ እየከፈሉና ገንዘቡ አንድ ላይ ተሰብስቦ ገቢ እየሆነ በየተራ ወይም በእጣ ለእያንዳንዳቸው እንዲደርስ ለማድረግ የሚያቋቁሙት ማህበር። 2.ለዚሁ ማህበር የሚከፈል ገንዘብ። *በየሳምንቱ እቁብ ይጥላል።*

እቁብ ደረሰው ተራው ደርሶ (እጣ ወጥቶለት) የተሰበሰበውን ገንዘብ ወሰደ።

እቁብ ገባ የእቁብ ማህበር አባል ሆነ።

እቁብ ጣለ በእቁብ ውስጥ ለሚሰበሰበው ገንዘብ የራሱን ድርሻ ከፈለ።

እቁብተኛ ቅ የእቁብ ማህበርተኛ ወይም አባል።

እቃ ስ 1.ተንቀሳቃሽ የመገልገያ መሳሪያ፣ ቁሳቁስ። 2.ጓዝ። 3.(ዘይ.) በራሱ አስተሳሰብ መሰረት የማይንቀሳቀስ፣ ደካማ፣ እንደፈለጉ ወዲያ ወዲህ የሚያደርጉት ሰው።4.(ዘይ.) የወንድንም ሆነ የሴትን አባለዘር በስሙ ላለመጥራት ተተክቶ የሚባል የማለዘቢያ ቃል።

እቃ ቤት ስ የእቃ ማስቀመጫ ወይም ማጠራቀሚያ ክፍል።

እቃ ግምጃ ቤት ስ 1.በአንድ መስሪያ ቤት ወይም ድርጅት ውስጥ ለአገልግሎት እንዲውሉ የተገዙ እቃዎች የሚቀመጡበት ቤት ወይም ክፍል። 2.በእቃ ግምጃ ቤት ውስጥ በሃላፊነት የሚሰራ ሰራተኛ።

እቅድ "አቀደ" ስር ተመ.

እቅጩን እርግጡን፣ እውነቱን።

እቅጩን ተናገረ እውነቱን፤ ትክክለኛውን ተናገረ።

እቅፍ "አቀፈ" ስር ተመ.

እቅፎሽ ገ.ከ.

እበት ስ 1.የቀንድ ከብት እዳሪ፣ ፍግ። 2.(ስድብ፣ ዘይ.) ሰነፍ፣ ጅል፤ የማይረባ።

እበት ጣለ ኩሳ (የቀንድ ከብት)።

እበጥ "አበጠ" ስር ተመ.

እቡይ ቅ ክፉ፣ ትእቢተኛ።

እባሽ "አበሰ" ስር ተመ.

እባብ ስ 1.እግር የሌለው፣ በልቡ እየተሳበ ወይም እየተንሻለለ የሚሄድ መርዘኛ አውሬ፣ ከይሲ። 2.(ዘይ.) ክፉ፤ ምቀኛ፣ ተንኮለኛ።

እባብ ዋጭ [አሞራ] ስ አንገቱ ረዥም፣ መልኩ ገብስማ የሆነና ብዙ ጊዜ እባብና ትላትል የሚመገብ የአሞራ አይነት።

እባክህ አንድ ነገር እንዲሆን፣ እንዲደረግ ለመጠየቅ ወይም ለመለመን ሲፈለግ ከሚጠየቀው ነገር ቀድሞ የሚነገር የልመና ማቅረቢያ ቃል። *እባክህ ስራውን ቶሎ ቶሎ ጨርስልኝ።*

እባጭ "አበጠ" ስር ተመ.

እብለት "አበለ" ስር ተመ.

እብሪት ስ ጥጋብ፣ ትእቢት፣ ማን አለብኝነት።

እብሪተኛ ቅ ጥጋበኛ፤ ትእቢተኛ።

እብቅ ስ ከእህል ላይ ተለይቶ የሚወጣ የደቀቀ ገለባ፣ ንፋሽ።

እብነበረድ ስ በተፈለገው ቅርፅና መጠን እየተስተካከለ ለተለያየ አገልግሎት (ለቤት፣ለሃውልት፤ ... ግንባታ) የሚውል፣ የተለያየ መልክ ያለውና ዋጋው ከፍተኛ የሆነ የድንጋይ አይነት።

እብደት "አበደ" ስር ተመ.

እብድ ገ.ከ.

እብጠት "አበጠ" ስር ተመ.

እቦኛ ቅ ክፉ፣ ጨካኝ፣ እቡይ።

እቴቴ ስ ታላቅ እህትን፤አክስትን፣...በአክብሮት ለመጥራት የሚያገለግል ቃል።

እቴጌ ስ የንጉሰ ሚስት የማእረግ ስም።

እትማማች "እህት" ስር **"እህትማማች"**ን ተመ.

እትም "አተመ" ስር ተመ.

እትራት "አተረ" ስር ተመ.

እትብት "አተበ" ስር ተመ.

እትት

እትትት አለ ግ ብርድ፡ ቆፈን የያዘው መሆኑን እትትት በማለት ገለፀ።

እትዬ ስ ዘመድ ወይም ቅርብ የሆነችን ሴት በአክብሮት ለመጥራት የሚያገለግል ቃል፡ ማንኛዋንም ሴት ለመጥራት ያገለግላል።

እቶን ስ የእንጨት እሳት የሚነድበት ጎድጓድ ያለ ትልቅ ምድጃ።

እችክ እችክ ቀዝቃዛ ውሃ ወይም ብርድ የነካው ሰው የሚያሰማው የመሰቀቅ ድምፅ።

እን— ከነጠላ ስም ጋር ተጣምሮ በመነገር ከነጠላው ስም ጋር ሊጎዳኝ የሚችለውን ስም ሁሉ አጠቃሎ ለመጥራት የሚያገለግል ምእላድ። *እነከበደ መጡ።*

እነሆ ይህው፡ ይህውና።

እነርሱ (እነሱ) በሶስተኛ መደብ ብዙ ቁጥርን የሚያመለክት ተውላጠ ስም።

እነዚህ (እነኚህ፡ እኚህ) በሁለተኛ መደብ የብዙ ቁጥር አመልካች ቅፅል ወይም ተውላጠ ስም። (አመ.ቅ.) *እነዚህ መፃሕፍት የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ላሳዳጊ ናቸው።* (አመ.ተ.ስ.) *የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ላሳዳጊ መፃሕፍት እነዚህ ናቸው።*

እነዚያ (እነኚያ፡ እኚያ) በሶስተኛ መደብ የብዙ ቁጥር አመልካች ቅፅል ወይም ተውላጠ ስም።

እና "-ና"ን ተመ.

እናት ስ 1.የወለደች ሴት ከወለደችው ጋር ባላት የተዛምዶ ግንኙነት የምትጠራበት ቃል፡ ወላጅ ። 2.ሴት ሞግዚት ወይም አሳዳጊ። 3.(ዘይ.) ደግ፡ ሩህሩህ።

እናት አልባ እናት የሌለው ወይም እናቱ የሞተችበት።

እናት አገር ስ የአንድ ሰው የትውልድ አገር።

እናንተ ተው.ስ. በሁለተኛ መደብ ብዙ ቁጥርን የሚያመለክት ተውላጠ ስም።

እኔ ተው.ስ. በአንደኛ መደብ ነጠላ ቁጥርን የሚያመለክት ተውላጠ ስም።

የእኔ ብጤ ደሃ፡ ለምኖ አዳሪ።

እንሰሳ "እንስሳ"ን ተመ.

እንሰት ስ ሰኑ ቆጮ የሚባለውን ምግብ ለማዘጋጀት የሚያገለግል፡ ቅጠሉ ሰፋፊ የሆነ የተክል አይነት፡ ኮባ።

እንስላል ስ እንጨቱ ውስጡ ክፍት የሆነና ቅጠሉ አረቄ አረቄ (የፈረንጅ) የሚሸት የተክል አይነት።

እንስራ ስ ከሸክላ አፈር የሚሰራ የጠላ መጥመቂያ ወይም የውሃ መቅጃና ማስቀመጫ እቃ(ስእሉን "ሸክላ እቃ" ስር ተመ.)።

እንስሳ (እንሰሳ) ስ 1.ማንኛውም ህይወት ያለውና በራሱ ሃይል ከቦታ ቦታ የሚንቀሳቀስ ፍጥረት። 2.እንደ ላም፡ በግ፡ ድኩላ፡... ያለ የቤትና የዱር ፍጥረት። 3.(ስድብ፡ ዘይ.) ሞኝ፡ ጅል፡ ቂል፡ የዋህ ።

የቤት እንስሳ ስ በቤት ውስጥና በቤት አካባቢ የሚኖር፡ ለሰው ልዩ ልዩ አገልግሎት የሚሰጥ እንደ ዶሮ፡በግ፡ፈረስ፡...ያለ ማንኛውም እንስሳ።

የእንስሳት ሃኪም ስ የቤት እንስሳትን በማከም ሙያ የሰለጠነ ሃኪም።

የዱር እንስሳ[አውሬ] ስ በዱር በጫካ የሚኖር እንደ አንበሳ፡ቀጭኔ፡ዝንጀሮ፡...ያለ ማንኛውም እንስሳ።

እንስት ስ የተባእት ተቃራኒ፡ ሴት።

እንስታይ ቅ ሴቴ።

እንሶስላ ስ ሴቶች እጅና እግራቸውን የሚያቀሉበት የእፅዋት አይነት።

እንሻፎ ስ ብርድ ወይም ውርጭ የመታው እህል።

እንሽላሊት (መንሽላሊት) ስ ጅራቷና ሰውነቷ እባብ የሚመስልና አራት እግር ያላት ትንሽ አውሬ።

እንሽላሊት

እንሽርት [ውሃ] ስ ለመውለድ በምጥ ላይ ካለች የሴት ብልት የሚፈስ እንደ ውሃ ያለ ፈሳሽ ነገር፡ "**ሽንት ውሃ**"ም ይባላል።

እንቀት ስ 1.የስንዴ ወይም የገብስ ክክ፡ ቅንጣው። 2.የእህል እንቅጥቃጭ።

እንቁ ስ በጣም ውድ የሆነና ለጌጥነት የሚያገለግል በባህር ውስጥ የሚገኝ የከበረ ድንጋይ፡ ሉል።

እንቁላል ስ 1.በአብዛኛው ከአእዋፍ ወገን የሆኑ እንስሳት የሚወልዱት፡ በስስና ጠንካራ ቅርፊት የተሸፈነ፡ ውስጡ በነጭ ፈሳሽ የተከበበ አስኳል ያለው እንክብል። 2.ፅንስ ሊሆን የሚችል ሴቴ ዘር።

እንቁላል መስኳል በጣም አምርቧታል።

እንቁላል ጣለች እንቁላል ወለደች (ዶሮ፡ ወፍ፡ ...)።

የእንቁላል ውሃ ስ በእንቁላል ውስጥ የሚገኝ ውሃ መሳይ ፈሳሽ ነገር፡ ዞፍ።

የቤት እንስሳት



1.አውራ ዶሮ
2.ፈረስ
3.ውሻ
4.ላም
5.ዶሮ
6.በቅሎ
7.ድመት
8.በግ
9. አህያ
10.ፍየል
11.ግመል
12.በሬ

የዱር እንስሳት

1.ዝሆን
2.አንበሳ
3.ነብር
4.ድብ
5.ካንጋሩ
6. ጥንቸል

የዱር እንስሳት

1

2

3

4

5

6


7

8

9

10

11

12

13

14

15

16

17

1.ነጭ ዝንጀሮ
2.ጥርኝ
3.ጉሬዛ
4.ኢንሹ
5.ጅብ
6.ጎሽ
7.ጦጣ
8.ፌቆ
9.የሜዳ ፍየል
10.ሳላ
11.ገረኑክ
12.ኢዋልድጊሳ
13.ፉደት
14ሴቾዌ
15.ቆሬ ፈረስ
16.አጋዘን
17.ሽለምጥማጥ

የዱር እንስሳት

1

2

3

4

5

6

11


8

10

7

9

12

13

14

15

1.ጉሬዛ
2.ዋልያ
3.እቆስጣ
4.ድኩላ
5.ቀበሮ
6.ሽኮኮ
7.ሚዳቋ
8.ቀጭኔ
9.ዳሊጋ አንበሳ
10.አነር
11. ሜዳ አህያ
12. አውራሪስ
13. ኒያላ
14. ወቦ ሸማኔ
15. ቆርኪ

እንቁልጭልጮሽ (እንቁልልጮሽ) ስ ልጆች አንድ ነገር ይዘው፣ ሳይሰጡ እያሳዩና እያጓጉ የሚናገሩት የጨዋታ ቃል።

እንቁራሪት ስ ጅራት የሌላት፣ በውሃ ውስጥና በየብስ መኖር የምትችል፣ ጡብ ጡብ እያለች የምትሄድ ትንሽ አውሬ፣ ጓጉንቸር።

እንቁራሪት

እንቁር ስ ከጠፍር ወይም ከእንጨት የተበጀ አናር፣ ጥንግ።

እንቁርባ ስ የአተር፣ የባቄላ፣ የሽንብራ፣... ፍሬ ልብስ፣ ገለባ፣ ገለፈት።

እንቁሽቁሽ "ቆሽቆሽ"ን ተመ.

እንቁጣጣሽ ስ 1.መስከረም አንድ ቀን የሚውል የዘመን መለወጫ በዓል፣ ቅዱስ ዮሃንስ፣ የአዲስ ዓመት የመጀመሪያ ቀን። 2.በአዲስ ዓመት መጀመሪያ ቀን ልጆች ለወዳጅ፣ ለዘመድና ለጎረቤት እንደ ገዘረከት የሚያቀርቡት እንግጫና አደይ አበባ፣ የአዲስ ዓመት የበጎ ምኞት መግለጫ ስጦታ።

እንቁጥቁጥ "*ቆጠቆጠ²" ስር ተመ.

እንቃሪ "*ነቀረ" ስር ተመ.

እንቃቅላ¹ ስ አራስ ልጅ።

እንቃቅላ² ስ እንደ እንሽላሊት ያለ የገበሎ አይነት።

እንቅልፋም "እንቀላፋ" ስር ተመ.

እንቅልፍ ዝ.ከ.

እንቅርት ስ በሰው አንገት ላይ ብዙውን ጊዜ በፊት ለፊት በኩል በጉሮሮ ላይ የሚወጣ እባጭ መሰል በሽታ።

እንቅርታም ቅ እንቅርት ያለበት ሰው።

እንቅሽ አለ "ነቀሸ" ስር ተመ.

እንቅሽ አደረገ ዝ.ከ.

እንቅብ ስ አስር ቁና ያህል የሚይዝ ከአክርማ ወይም ከሰንደዶ የሚሰራ ሰፊና ጎድጓዳ የስፌት እቃ (መጠኑ እንደየአካባቢው ይለያያል)(ስእሉን የስፌት እቃ ስር ተመ.)።

እንቅብ ሆድ (ስድብ) በርጫም።

እንቅጥቃጭ "ቀጠቀጠ" ስር ተመ.

እንቅፋት "*ነቀፈ" ስር ተመ.

እንቅፍድ "*ቀፈደደ" ስር ተመ.

እንቆቅልሽ ስ ድፍን ያለና ምስጢር አዘል ነገር (ጭውውት) በጥያቄ መልክ የሚቀርብበት የስነ ቃል አይነት።

እንቆቅልሽ ሆነ ምስጢሩ አልታወቅ አለ፣ ድፍን ያለ ነገር ሆነ።

እንቆቆ ስ ፍሬው ለኮሶ መድሃኒት የሚሆን፣ አብዛኛውን ጊዜ በወይና ደጋ የሚበቅል የእፅዋት አይነት።

እንቡር (እምቡር)

እንቡር አለ ግ ዘለለ፣ እመር አለ።

እንቡር እንቡር አለ ግ ዘለለ፣ እንጣጥ እንጣጥ አለ።

እንቡርባይ ስ "በረበረ" ስር ተመ.

እንቡስ "እምቡስ"ን ተመ.

እንቡሽቡሽ [ጠላ] ስ ቢጠጡት የማያስከር ጉሽ ጠላ።

እንቡቅቡቅ "*ቦቀቦቀ" ስር ተመ.

እንቡቡ

እንቡቡ አለ ግ ልጅን በጀርባ ላይ በአንቀልባ ወይም በልብስ አዘለ ወይም ተሸከመ።

እንቡጣ (እምቡጣ) ስ ጥጃዋ ሲሞት ላሟ ወተት መስጠቷን እንዳታቋርጥ የጥጃውን ቆዳ ጭድ ወይም ሳር ሞልተው በላሟ ፊት የሚያቆሙት የጥጃ ምስል፣ ጎፍላ።

እንቡጣጢያ (እምቡጣጢያ) ስ ስጋ፣ ጨቅላ።

እንቡጥ (እምቡጥ) ስ 1.እንደ ባቄላ፣ አተር፣ ሽንብራ፣... ያሉ የአበባ እህሎች አበባቸው ከረገፈ በኋላ በአበባው ቦታ የሚተካው የፍሬ አያያዝ ጅምር፣ ውጥን። 2.እንደ ባቄላ፣ አተር፣ ... ያሉ የአበባ እህሎች በእሸትነታቸው ጊዜ ፍሬውን ሽፍኖ ወይም ጠቅልሎ የሚይዘው ገለፈት። 3.ሲጋ ፣ ጮርቃ።

እንቡጥ ያህላል በጣም ትንሽ ነው።

እንቡጥ ጣለ ተክሉ አበባውን አራግፎ ፍሬ ማፍራት ጀመረ።

እንቡጭቡጭ "*ቦጨቦጨ" ስር ተመ.

እንቡፍና (እምቡፍና) ጠላ ስ ያልጠራና ያልፈላ ጉሽ ጠላ።

እንቢ (እምቢ) ተው.ግ. አይሆንም፣ እሻፈረኝ ወይም አላደርግም ለማለት የሚያገለግል ቃል ።

እንቢዮ ዝ.ከ.

እንቢታ ስ እሺ ወይም ይሁን አለማለት።

እምቢተኛ ቅ አልቀበልም፣ አላደርግም፣

ሳይሆንም ባይ።

እንቢ ኣለ ግ 1.ኣልቀበልም፣ ኣሻፈረኝ፣ ኣልታዘዝም፣ ... ኣለ። 2.ኣልሰራ፣ ኣልሆን ኣለ (እቃ፣ መሳሪያ፣...)።

እንቢ ነገር ስ የለሰለሰ ቁርበት እንደ ከረጢት ተሰፍቶ በውስጡ ገለባና ሳር ከተሞላበት በሗላ በአጋሰስና በኣህያ ጀርባ ላይ ከጭነት በታች የሚውል የጀርባ መከላከያ፣ መደላድል።

እንቢልታ (እምቢልታ) ስ በኣፍ የሚነፋ፣ ወፍራምና ቀጭን ድምፅ ማውጣት የሚችል፣ ከቀርከሃና ከብረት የሚሰራ እንደ ዋሽንት ያለ የሙዚቃ መሳሪያ(ስእሉን የሙዚቃ መሳሪያ ስር ተመ.)።

እንቢልታ ነፊ ስ በእንቢልታ መጫወት የሚችል ሙዚቀኛ።

እንቢልተኛ ዝ.ከ.

እንቢያጉስ ስ በጭነት በቅሉ ወይም በፈረስ ደረት ላይ የሚውል ከቀደሞሃይና ከቅናት ጋር የሚያያዝ የበቅሉ እቃ(ስእሉን "ኮርቻ" ስር ተመ.)።

እንባ "ኣነባ" ስር ተመ.

እንብርቢጣ ስ ብብት።

እንብርት (እምብርት) ስ 1.በሆድ መካከል የሚገኝ እትብት የሚቆረጥበት፣ ወደ ውስጥ ሰርጎድ ያለ ክብና ትንሽ የሰውነት ክፍል(ስእሉን ሰውነት ስር ተመ.)። 2.መሃል። *ቤቱ ከከተማው እንብርት ብዙም ኣይርቅ*።

እንብርት የለሽ በልቶ የማይጠግብ፣ ሆዳም።

እንብርክክ (እንብርክ) "*በረከከ" ስር ተመ.

እንብድብድ "*በደበደ" ስር ተመ.

እንቦሳ (እምቦሳ) ስ ከወተት በቀር ውሃ የማይጠጣና ሳር የማይበላ ያልጠነከረ ትንሽ ጥጃ።

እንቦሳ እሰሩ ወደ ኣዲስ ቤት ሲገባ "ቤት ለእንቦሳ" በማለት መልካም ምኞትን ለሚገልፁ እንግዶች በምላሹ የሚቀርብ የመልካም ምኞት መግለጫ።

እንቦቀቅላ (እንቦቃቅላ) ስ 1.ኣበባው ቅላት ያለው በወይና ደጋ የሚበቅል የእፅዋት ኣይነት። 2.ያልጠና፣ ለጋ (ልጅ፣ ቀንበጥ፣...)።

እንቧ (እምቧ)

እንቧ ኣለ ግ ጮሀ፣ ድምፅ ኣሰማ (በሬ፣ ላም)።

እንቧይ (እምቧይ) ስ ፍሬው ድቡልቡል የሆነና ሲበስል ሎሚ የሚመስል፣ እሾሃማና የማይበላ የእፅዋት ኣይነት፣ ፍሬውም እንቧይ ይባላል ።

እንቧጮ (እምቧጮ) ስ ቅጠሉ ለስላሳ፣ ኣገዳው ውስጠ ክፍት የሆነና ሲቀምሱት ጠው ጠው የሚል ጣእም ያለው የእፅዋት ኣይነት።

እንቶን "እንትና"ን ተመ.

እንትብትብ "*ተበተበ^{2}" ስር ተመ.

እንትና (እንተን፣ እንተኔ፣ እንቶኔ) የኣንድን ሰው ስም በራሱ ጊዜ ለስሙ ምትክ ወይም ልዋጭ ሆኖ የሚያገለግል ተውላጠ ስም። *እንትና መጣ*።

እንትን የኣንድን ነገር ወይንም እቃ ስም በረሱ ጊዜ ለስሙ ምትክ ወይም ልዋጭ ሆኖ የሚያገለግል ተውላጠ ስም። *እንትን ስጠኝ*።

እንትክትክ "*ተከተከ" ስር ተመ.

እንትፍ

እንትፍታ ስ የተተፋ ምራቅ፣ ኣክታ።

እንትፍ ኣለ ግ ኣክ ኣለ፣ ተፋ (ምራቅን፣ ኣክታን)።

እንትፍ እንትፍ ኣለ ግ ምራቅን በጥቂት በጥቂቱ በሚመረቀው ነገር ላይ በመትፋት ምርቃት ሰጠ፣ መረቀ።

እንትፍትፍ ኣለ ዝ.ከ.

እንቶ "ኢንቶ"ን ተመ.

እንቶ ፈንቶ የማይረባ፣ የማይጠቅም፣ ምናምን፣ ቅራቅንቦ ነገር።

እንቶኔ "እንትና"ን ተመ.

እንችፍ ስ የስንዴ ወይም የገብስ እንግውላይ፣ ግርድ።

እንከን ስ ጉድለት፣ ነውር፣ ፀያፍ፣ ሳንካ።

እንከፍ (መንከፍ) ቅ ቂል፣ ጅል፣ ሞኝ፣ ከርፋፋ።

እንከፍ እንከፍ ኣለ ግ ሲሄድ ጎፈፍ ጎፈፍ ዘርፈፍ ዘርፈፍ ኣለ።

እንኩሮ "ነኮረ" ስር ተመ.

እንኩቶ "ነኮተ" ስር ተመ.

እንኪያስ ቃ.ኣ. ታዲያ፣ እንግዲያማ፣ እንግዲያውስ።

እንካ ኣንድን ነገር በእጅ ይዞ ለሌላው ለመስጠት ሲፈለግ ተቀበል፣ ውሰድ፣ ያዝ ለማለት የሚያገለግል ቃል።

እንካ ሰላንቲያ ስ 1.በኣብዛኛው እረኞች ልጆች በጥያቄ መልክ እየተጠያየቁ የሚጫወቱት የቀልድ ጨዋታ። 2.ጭቅጭቅ፣ንትርክ፣...፣የስድብ ልውውጥ።

እንካ በእንካ መጠቃቀም፣ ሰጥቶ መቀበል።

እንካ ኣለ ግ ለመስጠት እጁን ዘረጋ፣ ውሰድ ኣለ።

እንክል

እንክል አለ ግ አንከስ አለ፥ ሽመድ ሽመድ አለ።

እንክርት (ም ፋ)

እንክርት (አንክርት) ስ 1.ከቦታ ቦታ ሊዘዋወር የሚችል ከሸክላ ወይም ከብረት የተሰራ ምድጃ። 2.የድርን አራዛ ለማጠንጠን ወይም ለማድራት አራቢው የሚወጠርበት መቃ፥ ቋሚንበ።

እንክርዳድ ስ 1.ከስንዴ ጋር አብሮ የሚበቅልና የፍሬው መጠን ከስንዴ የሚያንስ፥ ሲበሉት ወይም ጠላውን ሲጠጡት ራስ የሚያዞር ወይም የሚያስከር የአረም አይነት። 2.(ዘይ.) መጥፎ፥ ተፈላጊነት የሌለው (ሰው)።

እንክርፍ "*ከረፈፈ" ስር ተመ.

እንክብል "*ከበለለ" ስር ተመ.

እንክብካቤ "*ከበከበ^1" ስር ተመ.

እንክብክብ^1 ዘ.ከ.

እንክብክብ^2 "*ከበከበ^2" ስር ተመ.

እንክፍር "ከፈረረ" ስር ተመ.

እንኮኮ (እሽኮኮ) ስ ልጅን ማጅራት ላይ በማስቀመጥ ሁለት እግሮቹ በሁለት ትከሻ በኩል ደረት ላይ እንዲንጠለጠሉ ተደርጎ የሚያዝበት የአሸካከም አይነት (እኮኮ ወይም ኮኮ ይባላል)።

እንኮኮ (እሽኮኮ) አለ ግ ልጅን ማጅራት ላይ በማስቀመጥና ሁለት እግሮቹ በደረት ላይ እንዲንጠለጠሉ በማድረግ ተሸከመ።

እንኮይ ስ በወይና ደጋና በቆላ የሚበቅል፥ ፍሬው እንደወይን ሆኖ ከፍ ከፍ የሚልና የሚበላ የእፅዋት አይነት።

እንኳን 1.በአንድ ድርጊት ላይ የመደሰትና የመስማማትን ሁኔታ ለመግለፅና ደግ፥ እሰይ፥ አሹ ለማለት የሚያገለግል ቃል። *እንኳን አተረፈህ* 2.አንዱን ከሌላው ለማነፃፀር የሚነገር ቃል። *እንኳን እሱ አንተም አታልፍ*።

እንኳን ማርያም ማረችሽ (ምር.) አራስ ሴትን እሰይ፥ በደህና ወለድሽ፥ ተገላገልሽ ለማለት የሚነገር።

እንዘረዘይ ስ አበቃቀሉ እንደ ፈላ፥ ስሩ እንደ ሽንኩርት ያለና አበባው ቀይ የሆነ የእፅዋት አይነት።

እንዘጥ (እንዘጭ)

እንዘጥ አለ ግ ድንገት ወደቀ፥ እንቦጭ አለ(ብዙውን ጊዜ በቂጥ)።

እንዚራ ስ 1.ማንኛውም የሙዚቃ መሳሪያ የሚጠራበት የጥቅል ስም። 2.በገና የሚመስልና የሚነዝር አውታር ያለው የሙዚቃ መሳሪያ።

እንዛዝላ ስ 1.ወደፊትን ለማቅናት ወይም ለመግራት ሲባል በሚጓንቃው እንዲጎተተው የሚደረግ ረዥም ግንድ፥ ጅንግላ። 2.ሰድ፥ ባለጌ። 3.አልቃሻ።

እንዝህላል (ንዝህላል) ቅ 1.ግዴለሽ፥ ሃሳበ ቢስ። 2.ዝንጉ፥ ተላላ። 3.ስራ ፈት አውታታ።

እንዝርት ስ 1.እጀታው ከቀጭን ቀርከሃ ወይም ሽመል የሚሰራ፥ በራሱ ላይ ክብ የሆነ የቅል ስባሪ የተገጠመበትና ጫፉ ላይ የሚሰካ አነስተኛ ቆልማማ ሽቦ ያለበት የፈትል መሳሪያ። 2.ለስፌት መኪና በውስጥ በኩል የሚያስፈልገው ክር የሚጠነጠንበት የስፌት መኪና እቃ።

እንዝርት (ም ፋ)

እንዝዝ^1 ስ ጢንዚዛ።

እንዝዝ^2 ስ እበት እያድበለበለ የሚያንከባልል ከጥንዚዛ አነስ የሚል ነፍሳት።

እንገፍባን (እንጆባን) ስ ጫፉ ላይ ሽታ ያለው በሶብላ መሰል የእፅዋት አይነት።

እንዥቦ (እንጅቦ፥ እንጆሞ) ስ ሳይቀቀል ከእንጀራ ጋር የሚበላ ሁተታም የእፅዋት አይነት።

እንደ- 1. ከ በሃላ፥ ወዲያው። *እንደመጣ ይምጣ።* 2.መሆኑን፥-መደረጉን፥- መፈፀሙን፥...። *እንደሞተ አውቃለሁ/አለሁ እንደወሰደው ገብቶኛል።* 3. ለማድረግ፥ ለመፈፀም፥... መሞከሩን ለማሳየት የሚገባ ምእላድ። *እንደመተኛት አለ።* 4.የ-ያህል። *እንደአባት ያዋል።* 5.ከ ጋር ተመሳሳይ ነው፥-አይነት ነው፥...። *እንደ ወንድሙ ቀይ ነው/እንደ ሰማይ ይርቃል።* 6. ከመደብ፥ ከፆታና ከቁጥር መቀያየር ጋር መጠነኛ የቅርፅ ለውጥ እያደረገ ይገኝ፥ ይፈፀም፥...ዘንድ ለማለት በግስ ላይ የሚቀጠል ምእላድ። *እንዲመጣ ንገረው/እንድንራብ አንፈልግም።*

እንደሂሁላ (እንድሆህላ፥ እንዳሁላ) ስ ቁመቱ በአማካይ እስከ አንድ ክንድ ሊረዝም የሚችል፥ ግንዱ አቅመቢስ የሆነ፥ በጣም ወፍራምና ለስላሳ ቅጠል ያለው፥ በወይና ደጋ የሚበቅል አነስተኛ የእፅዋት አይነት።

እንዱሽዱሽ "*ዶሸዶሸ" ስር ተመ.

እንዲያው ተው.ግ. 1.ምንም ጥቅም ለሌለው፥ በባዶ፥ በከንቱ ለማለት የሚያገለግል ቃል። *እንዲያው ነው የለፋሽው*። 2.በነፃ፥ በብላሽ። *ባለሱቁ ወረቀቱን እንዲያው ሰጠኝ*። 3.እና። *እንዲያው ምን ይሻልሃል*?

እንዲያውም ተው.ግ. 1.በጭራሽ፥ ፈፅሞ።

እንዲያውም መጥቶ አያውቅም። 2.አማራጭ ሃሳብ ለማቅረቢያነት የሚያገለግል ቃል። *እንዲያውም ነገ እንሄዳለን*።

እንዳለ "አለ" ስር ተመ.

እንዳለ "ኣለ" ስር ተመ.

እንዴ የጥያቄን፥ የመገረምን ሃሳብ ለማስተሳሰፍ ከሌሎች ቃላት ጋር በመጣመር ሃሳቡን፥ ጥያቄውን፥... ለማጉላት የሚያገለግል ቃል። *እንዴ! ከየት መጣህ? /ትሄዳለህ እንዴ?*

እንዴታ ኣዎ፥ ነው ለማለት እርግጠኛነትን ለመግለፅ የሚያገለግል ቃል። *እንዴታ! መሄድ እፈልጋለሁ*።

እንዴት የአንድን ነገር ኣሰራር፥ ሁኔታ፥ ኣኳኋን ወይም ምክንያት ለማወቅ፤ እንዲሁም በሰላምታ አሰጣጥ ጊዜ የጤንነትን ሁኔታ ለመረዳት ጥያቄ የሚቀርብበት ቃል። *እንዴት ነበረ? /እንዴት መጣህ? እንዴት አደርክ?*።

እንድርሞሚት ስ ትልቅ ቀንጮና ረዥም ምንቃር ያላት ዥንጉርጉር የወፍ ኣይነት(ስእሉን ወፍ ስር ተመ.)።

እንዶድ ስ ቀጥ ብሎ መቆም የማይችልና እንደ ሃረግ የሚሳብ፥ ፍሬው ለልብስ ማጠቢያ የሚያገለግል የእፅዋት ኣይነት።

እንጀራ ስ 1.የበካ የጤፍ ወይም የስንዴ፥ የገብስ፥... ሊጥ ኣብሲት ከተጨመረበት በኋላ በሚፈለገው መጠን ቀጥኖ ምጣድ ላይ በሰፊውና በስሱ ክብ ሆኖ የሚጋገር (የሚሰፋ) ብዙ ኣይን ያለው ምግብ። 2.(ዘይ.) መተዳደሪያ፥ መኖሪያ።

እንጀራ ነሳ ኣደሀየ፥ ለችግር ዳረገ።

እንጀራ ወጣለት ሃብት ኣገኘ ወይም ባለፀጋ ሆነ።

[የ]እንጀራ ልጅ ስ ባል ወይም ሚስት ከሁለቱ ወይም ከሌላ ሰው የወለዱት ልጅ።

እንጀራ ቤት ስ 1.ቀደም ባለው ግዜ በነገስታትና መኳንንት ግቢ ውስጥ በተለይ እንጀራ የሚቀመጥበት ቤት ወይም የእንጀራ ቤት ሃላፊ። 2.በድግስ ወይም በግብዣ ጊዜ እንጀራ ለማቅረብ ወይም ለማደል የተመደበ አስተናጋጅ።

[የ]እንጀራ ኣባት ስ ሚስቱ ከሌላ ወንድ ለወለደችው ልጅ እንደሁለተኛ ኣባት የሚቆጠር ወንድ።

[የ]እንጀራ እናት ስ ባሏ ከሌላ ሴት ለወለደው ልጅ እንደሁለተኛ እናት የምትቆጠር ሴት።

[የ]እንጀራ እናት ጡጦ ስ ህፃናትን ለማባበል ኣፋቸው ላይ የሚደረግ ወተት መያዣ የሌለው ጡጦ።

የእንጀራ እናት ጡጦ

እንጀራ ጋጋሪ ስ ስራዋ እንጀራ መጋገር የሆነና በዚሁ የምትተዳደር ሴት።

እንጆባን "እንገፍባን"ን ተመ.

እንጂ ብዙውን ጊዜ እፍራሽ ሃሳብን የሚያስከትል ኣነፃፃሪ ምእላድ። *እሱ ጥቁር እንጂ ነጭ አይደለም/ይሞታል እንጂ ገንዘብ አይወጣውም/መጥቻለሁ እንጂ መች ቀረብሁ*።

እንጃ ቃ.አ. ስለ ኣንድ ነገር ኣለማወቅን፥ ጥርጣሬን፥ እንቢታን ለመግለፅ የሚነገር ኣሉታዊ ቃል። *መምጣቱን እንጃ*።

እንጆሳት ስ የምዝላት አፀት ወይም እናት፤ 6ኛ ኣያት።

እንጆልሽ ስ እጅግ በጣም ብዙ፥ እያሌ፤ ከብዛቱ የተነሳ ሰፍር ቁጥሩ የማይታወቅ የቁጥር መጠን።

እንጆሪ ስ 1.ግንዱ እንደ ሃረግ ያለ፥ ክብ ቅርፅ ያለውና ሲበስል ወይም በጣም ቀይ ሲሆን የሚበላ ፍሬ የሚያፈራ እሾሃማ የእፅዋት ኣይነት፤ ፍሬውም እንጆሪ ይባላል። 2. ቀጫጭንና ረዣዥም ቅርንጫፎች ያሉት፥ ሲበስሉ ቀያይ የሚሆኑና የሚበሉ ሞላላ ቅርፅ ያላቸው ትናንሽ ፍሬዎች የሚያፈራ የእፅዋት ኣይነት። ፍሬውም እንጆሪ ይባላል። 3.እንደቁጥቋጦ ሆኖ የሚበቅልና የሶስት ማእዘን ቅርፅ ያለው ሞላላ የሆነ ጣፋጭ ውሃ ያዘለ፥ ሲበስል በጣም የሚቀላና የሚበላ ፍሬ የሚያፈራ ተክል። የፈረንጅ እንጆሪም ይባላል።

እንገር ስ ላም፥ ፍየል፥... እንደወለደች የምትታለበው የመጀመሪያው ወፍራም ወተት።

እንጉርጉሮ "እንጎራጎረ" ስር ተመ.

እንጉዳይ ስ በክረምት የሚበቅልና ዣንጥላ የሚመስል ቅርፅ ያለው የእፅዋት ኣይነት።

እንጉዳይ

እንግሊላ (እንግላል) "*ጋለለ"ስር ተመ.

እንግሊዝ (ዘይ.) መስሪ፥ ማሽንክ።

እንግርግብ "*ገረገበ" ስር ተመ.

እንግት "ኣነገተ" ስር ተመ.

እንግውላይ "ገወለለ" ስር ተመ.

እንግዲህ (እንግዴህ) መ. 1.ታዲያ፥ እንኪያ። *እንግዲህ ምን ይሻላል ሁሉም ነገር አለቀ አለ*። 2.እንዲሁ፥ ይሁን። *ተመልከት! እንግዲህ በሽታው ተነሳበት*። 3.አሁን። *ምን*

ቀርቧል፤ እንግዲህ እንሂድ፡ 4.ከሁን በኋላ፥ ከሁን ጀምሮ። *እንግዲህ ወደየቤታችሁ ሂዱ*። 5.ዳግመኛ፡ ሌላ ጊዜ። *ደህና ሰንብት፤ እንግዲህ የምመጣ ላይመስለኝም*።

እንግዲህማ 1.አሁንማ። 2.ከሁን በኋላ።

እንግዲህም 1.አሁንም። 2.ከሁን በኋላም፡ እንደገና።

እንግዲህስ ስ 1.አሁንስ። 2.ከሁን በኋላ።

ከእንግዲህ [ወዲህ] ከሁን ጀምሮ፥ ከዚህ በኋላ።

እንግዲያ (እንግዲያማ፥ እንግዲያስ፥ እንግዲያውስ) 1 እንደዚያ ከሆነ። *እንግዲያ ወደቤቴ እሄዳለሁ*፡ 2-ታዲያ። *እንግዲያ ለምን ቁጭ ብለን አንጫወትም*።

እንግዳ "*ነገደ" ስር ተመ.

እንግዴ ልጅ ስ በእርግዝና ወቅት ከሽል ጋር በማህፀን የሚፈጠር፥ ፅንሱ በእትብት አማካይነት እየተመገበ የሚዳብርበትና ህፃኑ ከተወለደ በኋላ የሚወጣ አካል።

እንግጫ (ግጫ) ስ የዘመን መለወጫ ጊዜ ልጃገረዶች ከአበባ ጋር እየጎነጎኑ የመልካም ምኞት ስጦታ የሚያደርጉበት የሳር አይነት።

እንግፍጥ "*ገፈጠጠ" ስር ተመ.

እንጎቻ "*ነጎተ" ስር ተመ.

እንጎችት ዝ.ከ.

እንጣቆ (አንጣቆ) ስ በአገዳ እህል ቡቃያና በጎመን ላይ የሚገኝ መርዛማ ትል።

እንጣጢት ስ ተልባ።

እንጣጥ

እንጣጥ አለ ግ 1.ድንገት ዘለለ፥ እመር አለ። 2.(ዘይ.) ከአቅም በላይ ተንጠራራ።

እንጥል ስ በጉሮሮ ውስጥ ከላይኛው ጫፍ የተንጠለጠለችና ምላስ የምትመስል የሰውነት ክፍል። (ስእሉን "እፍ" ስር ተመ.)

እንጥል ወረደው እንጥሉ አበጠ፥ ታመመ።

እንጥልጥል "*ጠለጠለ" ስር ተመ.

እንጥርጣሪ "ጠረጠረ^{2}" ስር ተመ.

እንጥስታ "*ነጠሰ" ስር ተመ.

እንጥብጣቢ "ነጠበ" ስር ተመ.

እንጥፍጣፊ "*ጠፈጠፈ" ስር ተመ.

እንጦ^{1} (ህንጦ) ስ ገና አዲስ የተወለደ አራስ ልጅ።

እንጦ^{2} ስ 1.እንደቀብም ያለ ውስጠ ክፍት ነገር። 2.የሚያመነዥኩ እንስሳት ሁለተኛ ጉሮሮ፥ የምንገቢ መተላለፊያ።

እንጦርጦስ ስ መቃመቅ፡ ጥልቀቱ የማይታወቅ የጨለማ ጉድጓድ።

እንጨት ስ 1.የዛፍ ወይም የተክል ጠንካራው አካል። 2.ከዛፍ ላይ ተቆርጦ ለተለያየ አገልግሎት የሚውል የዛፍ ወይም የተክል ጠንካራው ክፍል።

እንጨት ሰበረ ሚካ ሃ.ዶ የማገዶ እንጨት ለቀመ ወይም ሰበሰበ።

የእንጨት ሽበት (ስድብ) ቅሌታም፡ ወራዳ (ምግባረ ብልሹ ለሆነ አዛውንት የሚነገር)።

እንጨት ፈላጭ ስ እንጨት በመፍለጥ ስራ የሚተዳደር ሰው።

እንጫጮላ ቅ እምቦቃቅላ፡ ለጋ፡ ያልጠና።

እንጭብሬ "*ጨበረረ" ስር ተመ.

እንጭብር ስ ቅጠሉ ሻካራ የሆነ አነስተኛ የሃረግ አይነት።

እንጭጭ ቅ ለጋ፥ ጮርቃ።

እንፉፍ ቅ ጅላጅል፡ ሞኝ፡ ቂል።

እንፉቅቅ "ፈቀቀ^{1}" ስር ተመ.

እንፉጭ ስ 1.ውርጭ የመታውና ፍሬው የተጨራመተ እህል። ቅ 2.(ዘይ.) ጅል፥ ሞኝ (ሰው)።

እንፋሎት ስ ከፈላ ውሃ ወይም እርጥበት ካለው መሬት ላይ በፀሃይ ሙቀት ምክንያት የሚነሳ ጭስ፥ ተን።

እንፍሌ ስ 1.የተቀቀለ ስጋ። 2.ከነእንቡጡ የተቀቀለ የበቆሎ ወይም የአተር እሸት።

እኚያ "እነዚያ"ን ተመ.

እኛ በአንደኛ መደብ ብዙ ቁጥርን የሚያመለክት ተውላጠ ስም።

እኛን ምሰል እኛ የምናደርገውን አድርግ ለማለት የሚነገር።

እኝ^{1} ስ ወንፊል።

እኝ^{2}

እኝ አለ ግ ጥርሱን አገጠጠ፡ ከንፈሩን ገልጦ ጥርሱንና ድዱን አሳየ።

እኝህ "እነዚህ"ን ተመ.

እኝኝ

እኝኝ አለ ግ 1.ዝናቡ ያለማቋረጥ ለረዥም ጊዜ ዘነበ። 2.ተነዛነዘ፥ ተጨቃጨቀ።

እኝኝ ብሳ ስ ከነሃሴ 28-30 ድረስ አፍኖና ካፊያ ሆኖ የሚሰነብትበት ሰሞን።

እኝያ "እኚያ" ን ተመ.

እከሌ "እገሌ"ን ተመ.

እከካም "አከከ" ስር ተመ.

እከክ ዝ.ከ.

እከየኛ ቅ እኩይ፡ ትእቢተኛ።

እከደከ (እከድእከድዬ፥ እከድዬ) መደነቅን፥ መገረምን ለመግለፅ የሚነገር ቃል። *እከደከ! ምነው ጉድ ሰራሀኝ*

እኩሊታ "አከለ" ስር ተመ.

እኩል ዝ.ከ.

እኩያ ዝ.ከ.

እክል ስ 1.ድንገተኛ ችግር። 2.ሃዘን፡ ለቅሶ።

እክር "አከረ^{1}" ስር ተመ.

እክታም "አከተ" ስር ተመ.

እክት ዝ.ከ.

እኮ (እኮን) ተው.ግ. 1.ከተለያዩ ቃላት ጋር በመጎዳኘት የሚነገር አጎላማሽ ምእላድ።*እኮ ስጠኝ /ከበደ እኮ ጎበዝ ነው፡* 2.እንጂ። *ተው እኮ፡* 3.ነውና፡ ነቡ እንጂ። *እንደነገርኩኝ ኢቃው እወነትም ጥሩ ነው። እኮ!*

እውር "አወረ" ስር ተመ.

እውቀት "አወቀ" ስር ተመ.

እውቂያ ዝ.ከ.

እውቅ ዝ.ከ.

እውን እውነት፡ እርግጥ።

እውነታ ስ 1.ሃቅ፥ እርግጥ፥ ትክክል። 2.በተጨባጭ ያለው ነገር ወይም ሁኔታ።

እውነት ዝ.ከ.

እውነተኛ ቅ 1.ሃቀኛ፡ የማይዋሽ። 2.ትክክለኛ፥ የሃሰት ያልሆነ። *እውነተኛ የብር ኖት፡*

እውከተኛ "አወከ" ስር ተመ.

እዚህ ቅ ቅርብ ወይም አጠገብ የሆነ ቦታን ወይም ተናጋሪው ያለበትን ስፍራ ለማመልከት የሚያገለግል ቃል። *እዚህ አገር ከገባሁ አስር ዓመት ሆነኝ/ ቤቱ ሩቅ አይደለም፣ እዚህ ጋ ነው፡*

ለዚህ ለዚህ ለሁሉ ለሌለው፥ ለማያረካ። *በጣም ውድ ነው ለዚህ ለዚህ ፒያሳ መግዛት ይሻላል።*

እዚሁ ለዚሁ ቅርብ፡*ቢታችን እዚሁ ለዚህ ሆኖ ብዙ አንገናኝም።*

እዚሁ በዚሁ አሁን በአሁኑ፥ በአንድ አፍታ።*እዚሁ በዚሁ ብሬን ሰረቁኝ፡*

እዚያና እዚያ ሩቅ ለሩቅ።

ያለዚያ(ያለዛ) የተባለው፥የተነገረው ካልሆነ።

በዚህ 1. የቅርብ አቅጣጫን ወይም ቀደም ሲል የተጠቀሰን ወይም የታወቀን ጉዳይ የሚያመለክት ቃል። *በዚህ በኩል አለፎ፡ በዚህ ምክንያት /በዚህ መሰረት/በዚህ ሁኔታ/እዚህ ነገር ውስጥ ሊታሰዝኑኝ...*።2.አንድን፡ተግባር፡ድርጊት፥...ለመፈፀሚያ የሚያገለግል እቃን፥ነገርን፥... የሚያመለክት ተውላጠስም። *በዚህ ገመድ እሰረው።*

በዚህ ላይ በተጨማሪ።

በዚህም በዚያም 1.በሁሉም በኩል፥ በሁሉም አቅጣጫ። 2.በማንኛውም አይነት፥ ምክንያት፥ ሁኔታ።

ከዚህ አሁን ካለንበት ቦታ፡ ሁኔታ፡ ነገር፡ ጊዜ፥... ለማለት የሚያገለግል ቃል።

ከዚህ ሌላ 1.ሌላ። 2.በተጨማሪ።

ከዚህ ቀደም ባለፈው ጊዜ፥ አሁን ካለንበት ጊዜ በፊት።

ከዚህ በኋላ አሁን ካለበት ቦታ፥ ሁኔታ፥ ነገር፥... ቀጥሎ።

ከዚህ ውጭ ከተባለው ወይም ከተጠቀሰው ሌላ።

ከዚህም በላይ በተጨማሪ።

እዚያ ሩቅ ቦታን ወይም አቅጣጫን ወይምአንድ የታወቀ ሁኔታን፥ጉዳይን፥... ለማመልከት የሚያገለግል ቃል። *እዚያ ብትጠይቅ ታገኘዋለህ/ እዚያ ጉዳይ ውስጥ አትግባ።*

በዚያ ሩቅ ቦታን ወይም አቅጣጫን ወይም የታወቀ ጉዳይን፡ ሁኔታን፥ጊዜን፥ ... አመልካች ቃል። *በዚያ ሂድ/ በዚያ ዘመን/በዚያ ጭቅጭቅ።*

እዚያ ላይ ወጣ 1.(ለዋጋ) ተወደደ። 2.ከፍተኛ ቦታ ላይ ሆነ፥ ደረሰ።

በዚያ በዚህ ብሎ እንደምንም።

ከዚያ 1.ከአንድ ነገር፥ ሁኔታ፥ ቦታ፥... ቀጥሎ። *ምሳ እንበላና ከዚያ ወደ ትቤት እንሄዳለን/በመጀመሪያ ላዲስ አበባ ሄደን ከዚያ ናዝሬት እንሄዳለን፡* 2.ወዲያ፥ እዚያ። *ከዚያ ማዶ ከሚታየው ቤት ውስጥ ነው የሚኖረው።*

ከዚያ በኋላ ከአንድ ነገር፥ ሁኔታ፥ ቦታ፥... ቀጥሎ።

ከዚያ በላይ በተጨማሪ።

እዝ "አዘዘ" ስር ተመ.

እዝል^{1} ስ ከሶስቱ ያሬዳዊ የዜማ አይነቶች አንዱ።

እዝል^{2} "አዘለ" ስር ተመ.

እዝን "አዘነ" ስር ተመ.

እየ—^{1} ከግስ ጋር በመጣመር አንድ ድርጊት በመካሄድ ላይ መሆኑን የሚገልፅ አሰር ምእላድ። *እየሄደ ነው፡*

እየ—^{2}

እያንዳንዱ "አንድ" ስር ተመ.

እዩዩ

እዩዩ አለ አለቀሰ፣ አነባ።

እይታ ስ 1.አስተያየት፥ አመለካከት። 2.ገፅታ።

እደላ "**አደለ**" ስር ተመ.

እዳ ስ 1.ብድርን፥ ቅጣትን፥ ካሳን፥... የሚመለከት ክፍያ። 2.(ዘይ.) ችግር፥ ስቃይ። *እዳዬን አየሁ።*

ምን እዳዬ/ተዳዬ ምን ቸገረኝ፥ ምን እዳ አለብኝ፥ እኔን ምን አገባኝ።

በእዳ ተነከረ እዳ ውስጥ ገባ፥ ባለእዳ ሆነ።

በእዳ ያዘ እዳ ያለበትን ሰው ወይም ንብረቱን በመያዝ እዳውን እንዲከፍል ጠየቀ፥ አስገደደ።

እዳ በእዳ ሆነ እዳ በዛበት ወይም እዳ ተጠማመረበት።

እዳ ከሜዳ ያልታሰበ ያልተጠበቀና ይመለከተኛል የማይሉት ችግር ወይም እዳ።

እዳ ሰርጉ እዳ የማይከብደው ወይም የማያስጨንቀው።

እዳሪ ስ 1.ከዚህ በፊት ታርሶ የማያውቅ ወይም በርከት ላሉ አመታት ሳይታረስ የቆየ መሬት። 2.ሰገራ፣ ኩስ። 3. ከቤት፣ ከግቢ ውጪ፣ ሜዳ፣ ደጅ።

እዳሪ ወጣ ተፀዳዳ።

እዳሪ አወጣ ለእርሻ ስራ ውሉ የማያውቀውን ወይም ረዘም ላሉ አመታት ሳይታረስ የቆየውን መሬት አረሰ፣ አለማ።

እዳሪ መሬት የ"**እዳሪ**"ን 1ኛ ፍቺ ተመ.

እዳይት (እድያት) ስ በነጠላ፣ በጋቢ፣ በቀሚስ፥... ጠርዝ ወይም ክፈፍ ላይ ለጌጥ የሚሰራ የተለያየ ቀለም ያለው ጥለት።

እድለኛ "**አደለ**" ስር ተመ

እድሳም ዝ.ክ.

እድል ዝ.ክ.

እድመኛ "**አደመ**^{2}" ስር "**እድምተኛ**"ን ተመ.

እድሜ ስ ከተወለዱበት እለት ጀምሮ ያለ ዘመን ወይም ጊዜ።

በእድሜ ገፋ አረጀ፥ ሸመገለ።

እድሜ አገኘ ብዙ ዘመን ኖረ፣ ቆየ።

እድሜ የለውም ብዙ አይቆይም፥ ቶሎ ያልቃል፣ ይሞታል።

እድሜው በሰለ ነፍስ አወቀ፣ አደገ።

እድሜው አጠረ ያለጊዜው ቶሎ ሞተ፣ ተሰበረ (ለሰው፥ ለእቃ፣...)።

እድሜ ልክ 1.እስከ እለተ ሞት። 2.ሁልጊዜ።

እድሜ ይፍታህ ስ እስከ እለተ ሞት ድረስ በእስር የሚያቆይ ፍርድ።

እድምተኛ "**አደመ**^{2}" ስር ተመ.

እድሞ ስ 1.የከብት ወይም የግምብ አጥር። 2.በአጥር በር ላይ የተሰራ ቤት። 3.ለአጥር በር የተሰራ ጣሪያ።

እድር ስ 1.የአንድ አካባቢ ሰዎች ችግራቸውን በህብረት ለመወጣት የሚያቋቁሙት የመረዳጃ ማህበር (በአብዛኛው ለሞት ጊዜ)። 2.ልማድ። 3.ማህበር፥ ቡድን።

እድር ለፋፊ ስ ለቅሶ ባለ ጊዜ እድርተኞች እንዲሰበሰቡ ጥሩንባ በመንፋት እየዞረ የሚናገር ሰው።

እድርተኛ ስ የእድር አባል።

እድሳት "**አደሰ**" ስር ተመ.

እድያት "**እዳይት**"ን ተመ.

እድገት "**አደገ**" ስር ተመ.

እድፋም "**አደፈ**" ስር ተመ.

እድፍ ዝ.ክ.

እጀታ "**እጅ**" ስር ተመ.

እጀኛ ዝ.ክ.

እጅ ስ 1.ከትከሻ እስከ እጅ ጣት ድረስ ያለው የሰውነት ክፍል። 2.ከእጅ መዳፍ እስከ ጣት ድረስ ያለው አካል። 3.ከአንድ ሙሉ ነገር ውስጥ የተወሰነው ክፍል። *ሃብቴን ሁለት ቦታ ከፍዬ አንዱን እጅ ለድሆች ሰጠሁ።*



እጅ 2ኛ ፍቺ

እጀ ሰባራ አደረገ ጥራት የሌለው ወይም ስራውን የማያስመሰግን ሆነ (የተሰራው ስራ)።

እጁ ረጠበ ገንዘብ አገኘ።

እጀ እርጥብ ቅ ገንዘብ የማያጣ።

እጁ ቀዳዳ ነው ገንዘብ አይበረክትለትም።

እጁ አመድ አፋሽ ነው ውለታው አይቆጠርለትም፣ አይመሰገንም።

እጁ አቆመ መስጠቱን ተወ፥ አቋረጠ (ገንዘብ ወይም ሌላ ነገር)።

እጁ አጠረ 1. ገንዘብ አጣ፥ ተቸገረ።

ገንዘብ ላነሰው (አንድ ነገር ለማከናወን)።

እጀ አጭር ቅ ድሃ፣ ችግረኛ።

እጁ ወርቅ ነው ጥሩ የእጅ ሞያ አለው።

እጁ ጣለው ውለታ ለዋለለት ወይም ጥሩ ስራ ለሰራለት ሰው መጥፎ በመስራቱ መጥፎ ነገር ወይም ጉዳት አጋጠመው።

እጁን ሰበሰበ መጥፎ ነገር ከመስራት ተቆጠበ፣ አደብ ገዛ።

እጁን በእጁ ቆረጠ በገዛ ወገኑ ላይ ጉዳት አደረሰ።

እጁን በደም ነከረ በግፍ የሰው ህይወት አጠፋ።

እጁን አነሳ 1.ተወ፣ ለቀቀ። 2.ተሸነፈ፣ የመሸነፍ ምልክት አሳየ።

እጁን አወጣ 1.ራሱን ቻለ። 2.አመለጠ (ከችግር)።

እጁን ከብብቱ አገባ ሰነፈ፣ ያለ ስራ ተቀመጠ።

እጁን ዘረጋ ሰጠ፣ ቸረ፣ ለገሰ።

እጁን ጫነበት ያዘው፣ ለመውሰድ ወይም የግሉ ለማድረግ ፈለገው።

እጅ መታ የሌላን ሰው የውስጥ እጅ በመምታት ማለ።

እጅ ሰጠ 1.ተማረከ፣ በቁጥጥር ስር ዋለ። 2.ተሸነፈ፣ ተዳከመ (በበሽታ፣ በችግር፣...)።

እጅ በዛበት ወሳጁ ወይም ተካፋዩ በዛ፣ በብዙ ሰው ተነካካ።

እጅ ተጣፋ ተማማለ።

እጅ ነሳ ሰላምታ አቀረበ።

እጅ አስነሳ 1.የአክብሮት ሰላምታ ተቀበለ። 2.ከባለስልጣን ዘንድ ቀርበው እጅ እንዲነሱ ወይም ሰላምታ እንዲሰጡ አደረገ። 3.ሰዎች እሱን እንዲለማመጡት ወይም እንዲያከብሩት አደረገ።

እጅ አስገባ 1.ተባበረ፣ ተሳተፈ። 2.ያዘ፣ ወሰደ።

እጅ አላስገባም አለ ለማረም ወይም ለማጨድ አስቸገረ (አረም)።

እጅ አዛወረ አንድን ይዞታ ከአንዱ ወደ ሌላው አስተላለፈ።

እጅ አደረገ ያዘ፣ ወሰደ፣ ተረከበ።

እጅ እጅ አለ 1.ጣእሙ ተበላሸ (ምግብ)። 2.ሰለቸ፣ አስጠላ (ነገር)።

እጅህን አውሰኝ ስለእኔ ሆነህ ምታልኝ፣ በልልኝ።

እጅ ያስቆረጥማል በጣም ይጣፍጣል።

የእጁን ሰጠው እንደ መጥፎ ስራው መጥፎ ነገር አጋጠመው።

የእጅ አመል አለበት ሌባ ነው፣ የመስረቅ ልምድ አለበት።

በእጁ ሄደ ጉቦ ሰጠ።

በእጅ አለ ገ.ከ.

በእጅ አደር በእጅ ያለ፣ የተያዘ።

በእጁ አደሬ ቅ ባለው የእጅ ሙያ (እውቀት) እየሰራ የሚተዳደር።

እጅ በእጅ ተው.ግ. 1.በአንድነት፣ በህብረት፣ በመረዳዳት(ለስራ)። 2.ክፍያው ወዲያውኑ የሚፈፀምና ዱቤ ያልሆነ።

እጅ ከፍንጅ ተው.ግ. አንድን ወንጀለኛ ወንጀል በመፈፀም ላይ እንዳለ የመያዝ ሁኔታ።

እጀ መርዝ ቅ የመታው ወይም የቆሰለው ቶሎ የማይድን።

እጀ መናኛ ቅ የሰው ንብረት የሚወስድ።

በእጀ መናኛ በጉቦ ወይም በእጅ አዙርና በገንዘብ የሚፈፀም (ህገ ወጥ ድርጊት)።

እጀ ሙሉ ቅ 1. ቸር፣ ለጋስ። 2.ባለረጅም እጅጌ (ለልብስ)።

እጀ ሰብ (እጀ ሰብእ) ስ መተት፣ ድግምት፣ ስራይ።

እጀ ሰፊ ቅ ቸር፣ ለጋስ።

እጀ ብልህ ቅ ጥበበኛ፣ የእጅ ስራ አዋቂ።

እጀ ደረቅ ቅ የቆረጠው ተክል መልሶ የማያቆጠቁጥለት ወይም የሚደርቅበት።

እጀ ጠባብ ስ እጅጌው ጠባብና ረጅም፣ ቁመቱ ከጉልበት ቢታች የሚወርድ፣ ከጎንና ከጎኑ ከላይ እስከታች ድረስ ስንጥቃት ወይም ክፍተት ያለው ልብስ።

[የ]እጀ ጠብቅ ዋስ ስ እገሌ ለህይወቴ ያስጋኛል ብሎ ለዳኛ ያመለከተ ሰው ባላጋራው ለአመልካቹ የሚጠራለት ዋስ።

እጅ መንሻ ስ አንድ ነገር እንዲደረግለት የፈለገ ሰው ለባለስልጣን የሚሰጠው ስጦታ ወይም ገፀበረከት።

እጅ ማሟሻ ስ በዳግም ትንሳኤ ማግስት የሚውለው ቀን (ሰኞ) የሚጠራበት ስም (ስራ የሚጀመርበት ቀን)።

እጅ አዙር ስ አንድን ድርጊት በሰውር በሌላ ሰው እንዲፈፀም ማድረግ።

እጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ስ አንድን አገር በፖለቲካ ስልጣን በኩል ነፃ አድርጎ በኢኮኖሚው በኩል ጥገኛ የሚያደርግ የቀድሞ ቅኝ ገዢዎች አዲሱ የብዝበዛ ፖሊሲ።

እጅ ጥበብ የእጅ ሙያ+ እውቀት።

የእጅ መብራት ስ ባትሪ።

የእጅ ሙያ ስ እንደ ጥልፍ፣ሽክላ ስራ+ አናጢነት፣... ያለ በእጅ የሚሰራ ስራ ችሎታ+ እውቀት።

የእጅ ስራ ስ 1.የእጅ ጥበብን የሚጠይቅ እንደ ስፌት+ ሸክላ+ ጥልፍ+... ያለ ስራ። 2.በመርፌና በክር የሚሰሩ እንደ ጥልፍ፣ ዳንቴል የመሳሰሉ ስራዎች።

የእጅ ሰአት ስ አምባር መዋያ ላይ የሚታሰር ሰአት።

የእጅ ሹራብ ስ 1. ከጥጥ ወይም ከሱፍ የሚሰራ የእጅ መሸፈኛ፣ ጓንት። 2.በፋብሪካ ሳይሆን ሰዎች በቤት ውስጥ በእጃቸው የሚሰሩት ሹራብ።

የእጅ ባትሪ "ባትሪ^{2}" ን ተመ.

የእጅ ቦምብ ስ መጠኑ አነስተኛ የሆነ በእጅ የሚወረወር ቦምብ።

የእጅ ኳስ ስ ኳስን በእጅ በመቀባበልና በመሬት ላይ በማንጠር ብቻ ግብ ለማግባት የሚደረግ የውድድር ስፖርት።

የእጅ ውሃ ስ ለእጅ መታጠቢያ የሚቀርብ ውሃ።

የእጅ ፅሁፍ ስ በፅህፈት መሳሪያ (በቀለም+ በብእር+...) አማካይነት በእጅ የተዘጋጀ ፅሁፍ።

እጀታ ስ የመጥረቢያ+ የጎራዴ+... መያዣ።

እጀኛ ቅ ሌባ+ ቀማኛ፣ ዘራፊ።

እጅጌ ስ በእጅ በኩል ያለና እጅ የሚገባበት የልብስ ክፍል።

ባለእጅጌ ቅ አጭር ወይም ረጅም እጅጌ ያለው፣ ሸምኒ ወይም እጀጌ ጉርድ ያልሆነ (ልብስ)።

እጅጌ ሙሉ ቅ ከትከሻ አንስቶ አምባር መዋያ ድረስ የሚጠለቅ እጅጌ ያለው(ልብስ)።

እጅጌ ጉርድ ቅ እጅጌው ከትከሻ እስከ ክርን አካባቢ ድረስ ብቻ የሆነ(ልብስ)።

እጅሳት **"አጀለ"** ስር ተመ.

እጅጌ **"እጅ"** ስር ተመ.

እጅግ ቅ 1.ብዙ፣ አያሌ። 2.በጣም። *እጅግ ትልቅ ነው*።

እጅጉን ተው.ግ. በጣሙን፣ በእያሌው (ለስላምታ የሚነገር)።

እጅግም ነው ብዙም አይደለም፣ በጥቂቱ ነው።

እገሌ (እከሌ) ተው.ስ. ስሙ በተዘነጋ፣ ባልታወቀ ወይም ስሙን ለመጥራት ባልተፈለገ ሰው ስም ምትክ እየገባ የሚነገር።

እገዛ **"አገዘ"** ስር ተመ.

እገዳ **"አገደ"** ስር ተመ.

እግል^{1} **"አገለ^{1}"** ስር ተመ.

እግል^{2} **"አገለ^{2}"** ስር ተመ.

እግር ስ 1.ለመሄጃ + ለመራመጃ፣ ለመቆሚያ የሚያገለግል የሰውነት ክፍል (ሰእሉን ሰውነት ስር ተመ.)። 2.ከብረት+ ከእንጨት+... የሚሰራ የወንበር፣ የአልጋ+... መቆሚያ።

በእገሌ እግር በእገሌ ምትክ+ ቦታ።

በእግር በፈረስ በብዙ አቅጣጫ በመሄድና በመልፋት፣ በጉጉት+ በጥብቅ በፍለጋ ። *በእግር በፈረስ ስለምትፈለግ ቶሎ ድረስ።*

እግሩን ዘረጋ ሰነፈ+ በዛነ።

እግሬ አውጪኝ አለ ተፈተለከ፣ ሮጠ (ከአንድ ነገር ለማምለጥ)።

እግር ሳሰ/ ሳመ ተለማመጠ።

እግር በእግር ወዲያው እንደሄደ፣ እንደወጣ፣ ሳይቆይ+ ተከታትሎ።

እግር አወጣ ዘዋሪ ሆነ።

እግር እስኪነቃ ቢኬድ ቢዞር፣ ቢለፋ።

እግር ከወርች ታሰረ ሁለቱ እግሩ ከአንድ እጁ ጋር ታሰረ።

እግር ጣለው ሳይታሰብ ድንገት ደረሰ።

እግረ መልስ ስ የከበለለን ሰው ወይም የጠፋን ከብት ወደ ቤቱ እንዲመለስ ያደርጋል ተብሎ የሚታመንበት ድግምት ወይም መተት።

እግረ መንገድ ተው.ግ. በዚያው። *እግረ መንገድህን ያንን እቃ ይዘህልኝ ና /እግረ መንገዴን አንድ ጥያቄ ልጠይቅዎት*።

እግረ ሙቅ ስ እግር ብረት።

እግረ ቀላል ቅ ፈጣን፣ ችኩል (ለአካሄድ)።

እግረ እርጥብ ቅ እድለኛ፣ ገዳም።

እግረ ደረቅ ቅ በሄደበት ወይም በደረሰበት የማይቀናው፣ እድለ ቢስ።

እግረ ጭራሮ ቅ በጣም ቀጭን እግር ያለው (ሰው)።

እግረ ፀሃይ ስ የፀሃይ ጨረር ወይም አውታር።

እግር ብረት ስ ጥፋት ያጠፋ ወይም ወንጀል የፈፀመ ሰው እግሩን የሚታሰርበት ብረት፣ እግረ ሙቅም ይባላል።

እግር ተከል ቅ መቆም የጀመረ (ህፃን ልጅ)።

የእግር መንገድ ስ 1. ለእግረኞች ብቻ የተፈቀደ መንገድ። 2.መኪና የማይገባውና በእግር ብቻ የሚያስኬድ መንገድ።

የእግር ኳስ ስ አስራአንድ አስራ አንድ

ተጫዋቾች በያዙ ሁለት ቡድኖች መካከል ኳስን በእግር እየመቱና እየተቀባበሉ ወደ ተቃራኒ ቡድን ግብ (ጎል) ለማግባት የሚደረግ ጨዋታ፣ ኳሱም የእግር ኳስ ይባላል።

የእግር ውሃ ስ ለእግር መታጠቢያ የተዘጋጀ ውሃ።

እግረኛ ቅ 1.በመጓጓዣ አገልግሎት የማይጠቀም፥ በእግሩ የሚጓጓዝ። 2.ዘዋሪ፣ ከውካዋ።

እግረኛ [ወታደር] ስ የነፍስ ወከፍ መሳሪያ በመያዝ የምድር ላይ ውጊያ የሚያካሂድ ወታደራዊ ክፍል።

እግረኛ [ጦር] ዝ.ክ.

እግት "**አገተ**" ስር ተመ.

እግዚአብሔር (እግዜር) ስ አለማትን የፈጠረና የሚቆጣጠር፥ መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው፥ የሁሉ በላይ የሆነ አምላክ።

እግዜር ይስጥልኝ (ምር.) አንድ ነገር ለሰጠ ወይም ላደረገ ሰው የሚቀርብለት የምስጋና ቃል።

እግዜር ይይለት (እር.) እግዜር ይፍረድበት።

የእግዚአብሔር ሰላምታ ስ ሰዎች በሚገናኙበት ጊዜ እንደምን አደርክ፥ እንደምን ሰነበትክ፡ እግዚአብሔር ይመስገን፡... በማለት የሚለዋወጡት ሰላምታ።

እግዚኦ ቃ.አ. 1.አቤቱ ጌታዬ ብሎ ለፈጣሪ የሚቀርብ የልመና ወይም የመማፀኛ ቃል። 2.አድናቆትን፡ መገረምን ለመግለፅ የሚነገር ቃል።

እግዚእታ ስ ለፈጣሪ የሚቀርብ አቤቱታ፣ ፀሎተ ምህላ።

እግዜር "**እግዚአብሔር**"ን ተመ.

እግድ "**አገደ**" ስር ተመ.

እጓለማውታ(ብ.ቁ **እጓለማውታን**) ስ እናት አባት የሞቱበት ልጅ፤ ድሃ አደግ።

እጢ[1] ስ እንደ እበጥ ወይም እንደ ኳስ ድቡልቡል የሆነ ቅርፅ ይዞ በሰውነት ላይ የሚወጣ የህመም አይነት።

እጢ[2] ስ የተለያዩ የሰውነት ክፍሎች ተግባራቸውን በጥሩ ሁኔታ እንዲያከናውኑ የሚረዳ ፈሳሽን በማመንጨት ወደየክፍሎቹ በደም አማካኝነት የሚያስተላልፍ ውስጣዊ የሰውነት አካል።

እጢው ዱብ አለ ደነገጠ፥ ከው አለ።

እጣ ስ 1.እድል። 2.ድርሻ፡ ፈንታ። 3.ከአንድ በላይ ከሆኑ ነገሮች መካከል አንዱን ከሌላው ለመምረጥ ሲያስቸግር ስምን በቁራጭ ወረቀት ፅፎ በመጠቅለል ወይም ቁርጥራጭ እንጨቶችን ለምርጫ በቀረቡት ነገሮች በመተካትና ከነዚህ መሃከል በመላ አንዱን በማንሳት ተመራጩን ለመለየት፥ ለመምረጥ የሚጠቀሙበት የምርጫ ዘዴ።

እጣ አወጣ ከተሰበሰቡት እጣዎች ወስጥ አንዱን አነሳ ወይም ባለእጣውን ለየ፥ አሳወቀ።

እጣ ጣለ 1.እጣዎች እንዲወጡ አደረገ። 2.እጣ አወጣ።

እጣ ተጣለ /ወጣ/ወደቀ በእጣ አንዱ ከሌላው ተለየ፡ ተመረጠ፤ የያንዳንዱ ድርሻ ተለይቶ ታወቀ።

እጣቢ "**አጠበ**" ስር ተመ.

እጣን ሞገር ስ በቅዳሴ መጨረሻ አካባቢ የሚባል የግእዝ ቅኔ አይነት።

እጣን "**አጠነ**" ስር ተመ.

እጥረት "**አጠረ**[1]" ስር ተመ.

እጥብጣቢ "**አጠበ**" ስር ተመ.

እጥፋት "**አጠፈ**" ስር ተመ.

እጥፍ ዝ.ክ.

እጣተኛ "**እጣ**" ስር ተመ.

እጦት ዝ.ክ.

እጨጌ ስ የደብረ ሊባኖስ ገዳም አስተዳዳሪ የማእረግ ስም።

እጩ "**አጨ**" ስር ተመ.

እጭ ስ ገና አዲስ የተፈለፈለና መንቀሳቀስ ያልጀመረ ንብ ወይም መሰል ነፍሳት።

እጮኛ "**አጨ**" ስር ተመ.

እፁብ ቅ አስገራሚ፡ አስደናቂ የሆነ።

እፅ(ብ.ቁ. **እፅዋት**) ስ በሳር፡ በቁጥቋጦ፡... መልክ የሚገኝ ማንኛውም ተክል።

እፀ መሰወር ስ አንድ ሰው እሱን ከያዘ ሰዎች ሊያዩት አይችሉም ተብሎ የሚታመንበት እፅ፤ መድሃኒት።

እፀ ምናሄ ስ ለተለያዩ በሽታዎች መድሃኒት ይሆናል የሚባልና በቆላ የሚበቅል የእፅዋት አይነት።

እፀ በለስ ስ የ"በለስ"ን አንደኛ ፍቺ ተመ.

እፀ ጳጦስ ስ ረግረግም ቅጠል ያለውና በዱር የሚበቅል የእፅዋት አይነት።

እፀፋርስ (እጣፋሪስ) ስ የትምህርት አብነት ይሆናል በማለት የቆሎ ተማሪዎች የሚቀምሱት የእፅዋት አይነት።

እፉኝት ስ ትንፋሹ ሰውን፡ ከብትን፡... በማሳበጥ ጉዳት የሚያደርስ የእባብ አይነት።

እፊያ ስ የመሶብ፡ የድስት፡... መክደኛ።

እፍ

እፍ አለ ግ ኃይለኛ ግፊት ያለው ትንፋሽ በአፉ በኩል ተነፈሰ (እሳትን ለማንደድ ወይም ለማቀፋፋት፣ የሻማ ብርሃንን ለማጥፋት፣ አቧራን ወይም ጉድፉን ለማስወገድ፣ ...)።

እፍ አሉ በጣም ተዋደዱ፤ ተቀራረቡ፣ ተፋቀሩ።

እፍ ያለ 1.የወጣለት፣ የታወቀ (ሽርሙጣ)። 2.በጣም ስስ የሆነ (ለምሳሌ ጨርቅ)።

እፍ ያለ ሜዳ አባጣ ጎርባጣ ያልሆነ፣ ለጥ ያለ ሜዳ።

እፍ እፍ አለ በወረት ወደደ፣ አፈቀረ።

እፍረት "**አፈረ**" ስር ተመ.

እፍንፍን "**አፈነ**¹" ስር ተመ.

እፍኝ "**አፈነ**²" ስር ተመ.

እፍግ "**አፈገ**" ስር ተመ.

እፎይ

እፎይታ ስ እረፍት፣ ከሃሳብ፣ ከድካም ግልግል።

እፎይ አለ ግ 1.አረፈ፣ ከድካም፣ ከሃሳብ ተገላገለ። 2.ተነፈሰ።

ኦ የ"**እ**" ራብዕ ሳብዕ ዘር።

ኦሞ ስ ልብስ፣ ለእቃ፣ ... ማጠቢያ የሚያገለግል በዱቄት መልክ የተዘጋጀ ሳሙና (ስያሜው ለማንኛውምየዱቄት ሳሙና ቢያገለግልም "**ኦሞ**" የአንድ አምራች ድርጅት የንግድ ምልክት ነው)።

ኦሪት ስ 1.በሙሴ የተፃፈ የእስራኤላውያን ወይም የእብራውያን ሃይማኖት ህግ። 2. በብሉይ ኪዳን ውስጥ የሚገኝና ከኦሪት ዘፍጥረት እስከ ኦሪት ዘዳግም ያለው አምስቱ የሙሴ መፅሃፍት።

ኦሪታዊ ቅ 1.የኦሪት ወይም የኦሪት ጊዜ። 2.በአስተሳሰቡ ኋላ ቀር የሆነ።

ኦርቶዶክስ ስ ከኒቂያ ጉባኤ በኋላ በክርስቶስ አምላክነት እምነታቸውን ያፀኑት ወገኖች የተሰጠ ተጨማሪ መጠሪያ።

ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ስ ቃልና ስጋ በተዋህዶ አንድ አካል፣ አንድ ባህርይ፣ አንድ ልጅ፣ ፍፁም አምላክና ፍፁም ሰው ሆነ የሚል ትምህርተ ሃይማኖት።

ኦርኬስትራ ስ የተለያዩ የሙዚቃ መሳሪያዎችን የሚጫወቱ ሰዎችንና ድምፃውያንን የያዘ የሙዚቃ ቡድን።

ኦርጋን ስ በጣት የሚነኩ ቁልፎችና በአየር ግፊት አማካይነት ድምፅ የሚሰጡ ብዙ ቧንቧዎች ያሉት የሙዚቃ መሳሪያ።

ኦቶሞቢል "አውቶሞቢል" ን ተመ.

ኦች (-ዎች) ብዙትን አመልካች ምእላድ። (ለምሳሌ አንበሳ→አንበሶች፣በሬ→በሬዎች)።

ኦዞን ስ የፀሃይ ጨረር በቀጥታ መሬት ላይ እንዳያርፍና ጉዳት እንዳያስከትል የሚከላከል፣ ምድርን ከሸፈናት ከባቢ አየር በላይ የሚገኝና ሃይለኛ ሽታ ያለው የኦክስጅን ንብርብር የሆነ ልባስ።

ኦፊ ያሬድ ስ ድምፀ መልካም ወፍ።

ኦፔራ ስ በሙዚቃና በዜማ በመታጀብ የሚቀርብ ድራማ።

ከ

ከ "አ" ፊደል ዘር ቀጥሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል (ግእዙ ሆሄ)።

ከ— መዋ. 1.መነሻን ለማሳየት የሚያገለግል ምእላድ። *ከጎንደር መጣ*። 2.ከተለያዩ ቃላት ጋር እየተጣመረ ጊዜን፡ ቦታን፡ ...። የሚያመለክት ምእላድ። *ከጠረጴዛው ስር/ከወንበሩ አጠገብ/ ከአሁን በፊት/ ከህንፃው ፊት ለፊት /ከጓደኛው ጋር*። መዋ. 2.ቅድመ ሁኔታን አመልካች ምእላድ። *እቃውን ከሰጠኝ ገንዘቡን እመልሳለሁ*። 3.አንድ ድርጊት ገና እንደተደረገ ወይም እንደተከናወነ ወዲያውኑ ለማለት የሚያገለግል ምእላድ። *ፍየል ከመድረሷ...*። 4.አንድ ድርጊት መከናወኑን ወይም መፈጸሙን ለማመልከት የሚያገለግል ምእላድ። *መንገዱ ከተሰራ ሁለት ዓመት ይሆናል*። 5.አመዛዛኝ ወይም አነፃፃሪ ምእላድ። *ብዙ ከመናገር ብዙ ማዳመጥን ይወዳል*።

ከሃዲ "ካደ" ስር ተመ.

ከለለ¹ ግ 1.ጋረደ (በአጥር፣ በወርቅ፣...)። 2.አወረ፡ አሳወረ፣ ማየት ከለከለ (አይንን)። 2.ወሰነ፡ ድንበር አበጀ።

ከለላ ስ 1.ግርዶሽ። 2.መከታ። 3.አጥር።

ከላይ ቅ ድንበር ወይም ወሰን እንዲለይ ወይም እንዲ ያበጅ የተመደበ ወይም የተመረጠ (ሰው)።

ክልል ስ 1.ወሰን ወይም ድንበር ተበጅቶለት ከሌላው ቦታ፣ አካባቢ እንዲለይ የተደረገ ቦታ ወይም አካባቢ። 2.ድንበር፡ ወሰን።

ተከለለ ግ 1.ድንበር ለየ። 2.ድንበርተኛ፡ ወሰንተኛ [illegible]።

አከለለ ግ 1.አዋሰነ። 2.ብዙ ቦታ ዞረ፡ አዳረሰ።

ከለለ² ግ እንደ ደወል ወይም መረዋ ያለ ድምፅ አሰማ፡ ጮኸ።

ኪል (ኪልል) አለ ግ የቃጭል ወይም የደወል ድምፅ አይነት አሰማ።

አከላላ ግ አቅራራ፣ ሸለለ፣ ዘፈነ።

ከለለ³ ግ በጣም ኳ ብሎ ደረቀ፣ ከሸለለ።

ከለለ⁴ ግ ቆረጠ፣ ሰየፈ (አንገትን)።

ከለላ "ከለለ¹**"** ስር ተመ.

ከለሜዳ ስ ቀይ ሃር ወይም ግምጃ።

ከለሰ¹ ግ ተምሮ ወይም አጥንቶ ያለፈውን እንደገና መልሶ አጠና።

ክለሳ ስ ተምሮ ያለፈውን እንደገና ደግሞ መማር።

ተከለሰ ግ በእውቀቱ ማነስ ምክንያት አልፎት የሄደውን የትምህርት ዘርፍ ወይም ክፍል ደግሞ እንዲማር ተደረገ።

አስከለሰ ግ ረስቶት የነበረውን ትምህርት እንደ ገና እንዲያጠናው አደረገ፣ ረዳ።

ከለሰ² ግ 1.ቀላቀለ፡ ደባለቀ፣ ቀየጠ። 2.ቻለሰ፣ በብዛት ጨመረ (ፊትሽን)።

መከለሻ [ቅመም] ስ ቁንዶ በርበሬ፣ ቀረፋ፣ ቅሩንፉድ፣ ጥምዝ፣... በአንድ ላይ ተወቅጦ የሚዘጋጅ የወጥ ቅመም።

ክልስ ቅ የተለያየ ዘር ካላቸው ሰዎች የተወለደ (ለምሳሌ ከፈረንጅና ከሃበሻ)።

ክልስ በርኖስ ስ በላዩ ላይ ፀጉር እየተነሰነሰ ውሃ ውስጥ በእግር እየታሸ እድላት እንዲያገኝ የተደረገ አርጌ በርኖስ።

ክልስ ጥይት ስ በአካባቢው የሚገኘውን ባሩድ ዋናው ፋብሪካ ከሰራው የጥይት ባሩድ ጋር በመቀየጥ የሚሰራ ሬጋ ሰራሽ ጥይት።

ከለበ ግ ተጣደፈ፣ ቸኮለ፣ ሮጠ።

ከላባ ቅ (ስድብ) ቀዥቃዣ፣ ክልፍልፍ፣ ከውካዋ።

ክላብ 1.ከላባ። 2.ውሻ።

ክልብልብ (ከለብላባ) ቅ (ስድብ) ክልፍልፍ፣ ቀዥ ቃዥ፣ ከውካዋ።

ተካለበ ግ 1. ተቻኮለ፣ ተጣደፈ። 2. ተክለፈለፈ፣ ተንቀዠቀዠ።

ተክለበለበ ግ ተክለፈለፈ፡ ተንከወከወ፣ ተንቀዠቀዠ።

አካለበ ግ 1.አቻኮለ፡ አጣደፈ። 2.አክለፈለፈ፣ አንቀዠቀዠ።

አክለበለበ ግ አክለፈለፈ፡ አንቀዠቀዠ፣ አጣደፈ።

ከለበሰ ግ 1.በአንድ ትንፋሽ ኸርው አድርጎ ጠጣ። 2.ደፋ፣ ቻለሰ፣ አፈሰሰ።

ከለብላባ "ከለበ" ስር **"ክልብልብ"**ን ተመ.

ከለቻ ስ የራስ ቁር፣ ጥሩር።

ከለከለ ግ 1.ነሳ። 2.አገደ፡ አቆመ፣ ገታ። 3.ጠበቀ፣ ሃይ አለ። 4.አጋፈረ፣ ተቆጣጠረ፣ በስነ ስርአት አስተናገደ።

ክልካይ ስ አጋፋሪ፡ በረኛ (የቤተ መንግስት)።

ክልክል ቅ የተከለከለ፣ ያልተፈቀደ።

ክልክል [ሳር] ስ ከብቶች ገብተው እንዳያበላሹት ወይም እንዳይበሉት ተብሎ ለብቻው ተከልሎ ወይም ታጥሮ የሚጠበቅና

ለድርቆሽ የሚዘጋጅ ሳር።

ተከለከለ ግ 1. እንዳይወስድ ወይም እንዳይጠቀም ተደረገ (አንድን ነገር)። 2.ታገደ። 3.እንዳይከናወን ተደረገ።

ተከላከለ ግ 1.አንድ ነገር እንዳይደረግ ወይም እንዳይፈፀም፣... ከለከለ። 2.ከሚሰነዘርበት አደጋ ራሱን ለማዳን ተጣጣረ፣ ሞከረ።

መከላከያ ስ 1.ምሽግ፣ ከለላ፣ አምባ። 2.የጦር መሳሪያ። 3.የሃገርን ድንበርና ሉአላዊነት የሚያስከብር ሰራዊት። 4.የወሊድ መቆጣጠሪያ ኪኒን።

መከላከያ ምስክር ስ ተከሳሽ የሚያቀርበው (የተከሳሽ) ምስክር።

ተከላካይ ቅ (ስፖ.) በራሱ ጎል ክልል የተቃራኒው ቡድን ተጫዋቾች የማጥቃት ጨዋታ እንዳያደርጉ የሚጠብቅ ተጫዋች።

አከላከለ ግ እንዳይደረግ ወይም እንዳይፈፀም አስደረገ፣ አስተወ።

***ከለወሰ**

ክልዋሳ ቅ ጎስቋላ፣ ከሲታ፣ ለዋሳ።

ተንከላወሰ ግ 1.ወዲያ ወዲህ አለ፣ ተላወሰ፣ ተንቀሳቀሰ። 2.አዘገመ።

መንከላወሻ ስ መላወሻ ወይም መንቀሳቀሻ (ቦታ፣ ገንዘብ)።

አንከላወሰ ግ 1.ወዲህ ወዲያ አሰኘ፣ አላወሰ፣ አንቀሳቀሰ። 2.አዘገመ። 3.አንገዋለለ። *በስነ ስርአት ብላ ምግቡን አታንከላውሰው።*

ከለፈ ግ ሰረቀ፣ ቀማ፣ ነጥቆ በረረ።

***ከለፈ**

ክላፋ ቅ (በድብ) ከውካዋ፣ ቀዥቃዣ።

ክልፍልፍ (ከለፍላፋ) ዝ.ከ.

ተክለፈለፈ ግ ተንከወከወ፣ ተንቀዠቀዠ።

አክለፈለፈ ግ አንከወከወ፣ አንቀዠቀዠ።

ከሊፋ ስ (እስል.) በቁራን ህግ መሰረት የመንግስት ወይም የሃይማኖት እንደራሴ ወይም ወኪል።

ከላ ግ አስወገደ፣ ዞር አደረገ፣ አነሳ።

ክላ ግ ዞር በል! ወግድ።

ከላበ "ከለበ" ስር ተመ.

ከላይ "ከለለ^1" ስር ተመ.

ከላፋ "*ከለፈ" ስር ተመ.

ከል ስ 1.ከቀንጠፋና ከብረት አር ይዘጋጅ የነበረ ጥቁር ቀለም። 2.ጥቁር ቀለም የተነከረ የሀዘን ልብስ።

ክልብ "ከለበ" ስር ተመ.

ክልካይ "ከለከለ" ስር ተመ

ክልዋሳ "*ከለወሰ" ስር ተመ.

ከመ—

ከመጤፍ አይቆጥረውም ከምንም አይቆጥረውም፣ ይንቀዋል፣ አያከብረውም፣ አይፈራውም፣...።

ከመቅፅበት ወዲያው፣ እጅግ በጣም አጭር በሆነ ጊዜ ውስጥ፣ በፍጥነት።

ከመእንስሳ (በድብ) ከእንስሳ የማይሻል፣ እንደ እንስሳ ያለ።

ከመረ ግ 1.አንዱን በአንዱ ላይ አነባበሮ አስቀመጠ። 2.ቆለለ።

ክምር ስ ቁልል።

ተከመረ ግ 1.ተቆለለ። (ዘይ.) አኮረፈ።

ተከመረበት በድንገት ዘሎ እላዩ ላይ ወጣበት ጉብ አለበት ። *በጫካ ውስጥ ሲሄድ ነብሩ በድንገት ተከመረበት።*

***ከመቸ**

ክምችት ስ ስብስብ፣ ጥርቅም።

ተከማቸ ግ ተሰበሰበ፣ ተጠራቀመ።

አከማቸ ግ ሰበሰበ፣ አጠራቀመ።

ከመከመ ግ ከረከመ፣ አስተካከለ፣ ደመደመ (ፀጉርን፣ ሳርን፣...)።

ከመክም [ጎፈሬ] ስ በደንብ ተስተካክሎ የተቆረጠና የተበጠረ ጎፈሬ።

ክምክም [ጎፈሬ] ዝ.ከ.

ከሙን ስ መልኩ እንደ ነጭ አዝሙድ ነጣ ያለ፣ ቅርፁ ቀጫጭንና ትናንሽ ሆኖ ከስንዴ ጋር ተመሳሳይነት ያለው፣ ብዙ ጊዜ ከመከለሽ ቅመም ድብልቆች አንዱ ሆኖ የሚያገለግል የቅመም አይነት።

ከማን አንሼ ቅ 1.ያለአቅሙና ያለማእረጉ ሌሎችን ለመምሰል የሚፈልግ ወይም የሚኮራ ሰው። ስ 2.እግር የሚያሳብጥ በሽታ፣ ኮብሽ።

ከምሱር ስ ሲተኮስ ቃታው የሚወጋው የጥይት ቀለህ ቂጥ፣ እምብርት(የጥይትን ስእል ተመ.)። 2.ለዘለበት ማስገቢያ ተብሎ በተዘጋጀ የቀበቶ፣... ቀዳዳ ዙሪያ የሚገባ ከነሃስ ወይም ከብረት፣... የሚሰራ ክፈፍ።

ከረመ ግ 1.የክረምትን ወራት አሳለፈ፣ ክረምት እስኪወጣ ቆየ ወይም ኖረ። 2.ሰነበተ፣ ቆየ።

ክርሞ ስ ወደፊት የሚመጣው ወይም የሚቀጥለው አመት።

ክርሞ ጥጃ ቅ የማይሻሻል፣ በያመቱ በመሻሻል ፈንታ እያሽቆለቆለ የሚሄድ።

ክራሞት ስ ኑሮ፣ አኗኗር።

ተከራረመ ግ በመቻቻል አብሮ ቆየ ወይም

ሰነዘተ፡ ተኗኗረ።

ተካረመ ዝ.ክ.

አካርሚኝ ስ 1.ለክረምት ወራት በመኖሪያነት የሚያገለግል ቤት። 2.ዋናው ቤት እስኪሰራ ድረስ ለመኖሪያነት የሚያገለግል አነስተኛ ቤት፡ መቃኞ።

ከረሜሳ ስ ከልዩ ልዩ ቅመማት፥ ፍራፍሬዎች፥ ስኳር፥... በተለያየ ቅርፅ፡ መጠንና አይነት የሚዘጋጅ ጣፋጭ።

ከረረ ግ 1.ደረቀ፥ ገረረ። 2.ጦዘ፥ ደበነ፥ ጠበቀ (ገመድ፡ ፈትል)። 3.ተነፋ፥ አበጠ፥ ተነረተ (ሆድ)። 4.ባሰ፥ አየለ፥ ፀና (ነገር፥ ፀብ፥..)። 5.አለመጠን ጮኸ፥ ተንጨረጨረ(ድምፅ)።

ከራራ ቅ 1.ደረቅ። 2.(ስድብ፡ ዘዬ.) አጭር፡ ድባኖ።

ክር ስ ለሰፌት፡ ለሹራብ፡ ለጸንቁል፥... ስራ የሚያገለግል ከጥጥ፡ ከሱፍ፡ ከናይለን፥... የሚዘጋጅ የከረረ ወይም የጦዘ ፈትል።

ክርር አለ ግ 1.ሞተ። 2.ወደቀ፥ፍንችር አለ። 3.ከረረ።

ተካረረ ግ ተባባሰ፥ አየለ፥ ጠነከረ (ነገር፥ፀብ፥...)።

ተካረሩ ግ የምር ተጣሉ።

አክራሪ ቅ በሚከተለው እምነትና አስተሳሰብ ውስጥ ፍፁምነት ሊኖር ይገባል ብሎ የሚያምንና የቆየውን እምነትና አስተሳሰብ ከዘመናዊው ሁኔታ ጋር ማስተካከልና ማጣጣም የማይፈልግ አጥባቂ (ሰው)።

ከረሸመ "ኮረሸመ"ን ተመ.

ከረበተ ግ 1.ጣለ፥ አጋደመ። 2.ገለበጠ፥ አፈሰሰ። 3.ሰነጠቀ፡ ገመሰ (እርሻን)።

ተንከረባበተ ግ ተገለባበጠ።

አንከረባበተ ግ ገለባበጠ፡ አደራረበ።

ከረባት "ክራባት"ን ተመ.

ከረቦ "ከበሮ"ን ተመ.

ከረተሰ ግ ከረተፈ፡ ሸረከተ፡ ከካ።

ክርትስ ቅ ክርትፍ፥ ሽርክት።

***ከረተተ**

ክርታታ (ክረትት) ቅ 1.ከቦታ ቦታ የሚዘዋወር፥ ቋሚ ቦታ የሌለው። 2.አውታታ፥ እንግልቱ።

ክርትት (ክርተት) አለ ግ ተንከራተተ።

ተንከራተተ (ተንከረተተ) ግ 1.ወዲያ ወዲህ በማለት ተንገላታ፥ ተጉላላ፡ ባዘነ። 2.ዞረ፡ ብዙ ቦታ ሄደ ወይም አዳረሰ።

አንከራተተ (አንከረተተ) ግ 1.አንገላታ፥ አጉላላ፡ አባዘነ። 2.አዞረ፥ ብዙ ቦታ እንዲሄድ ወይም እንዲያዳርስ አደረገ።

እንክርት (አንክርት) በፊደል ተራው ተመ.

ከረተፈ ግ 1.በትንሽ በትንሹ ቀረጠ፡ ቀረጠፈ። 2.ገረደፈ፥ ሸረከተ፡ ከካ።

ክርትፍ ቅ ግርድፍ፡ ሽርክት።

ከረቸመ ግ 1.አጥብቆ ገጠመ፡ ዘጋ፡ ቆለፈ። 2.ቸነከረ። 3.ጥቅጥቅ አድርጎ አጠረ (አጥርን)። 4.ቀፈደደ፥ ጠፈነገ፥ አጥብቆ አሰረ።

ክርችም አለ የ "ተከረቸመ"ን 1ኛ ፍቺ ተመ.

ክርችም ብሎ ዋለ ምንም ሳይቀምስ ወይም ሳይበላ ዋለ።

ተከረቸመ ግ 1.ግጥም ብሎ ተዘጋ፡ ተቆለፈ። 2.አንድ ቤት ወይም ክፍል ውስጥ ለረዥም ጊዜ ዘግቶ ተቀመጠ። 3.ያለ ጋብቻ ውል ከሴት ቤት ውስጥ በባልነት ለመኖር ገባ።

ተከርችም ስ ያለ ጋብቻ ውል ከሴት ቤት ውስጥ በባልነት ለመኖር የመግባት ድርጊት።

ተከርችም ገባ የ"ተከረቸመ"ን 3ኛ ፍቺ ተመ.

ከረነተ ግ አጥብቆ አሰረ፥ ጠፈነገ።

ከረኖ ግ በክርን መታ፥ ደሰቀ።

ክርን ስ የእጅ ረዢሙ አጥንቶች ከሚገናኙበት በስተ ጀርባ ያለ የሰውነት ክፍል፡ ኩርኝ(ስእሉን ሰውነት ስር ተመ.)።

ከረከመ ግ ለማሳጠር፡ ለማሳመር፥... ቆረጠ፥ አስተካከለ።

ከረከረ ግ 1.ገዘገዘ፡ መገዘ። 2.ክርክር አበጀ። 3.ከነከነ። *ጉሮሮዬን ይከረክረኛል*። 4.አጥብቆ፥ ሰርስሮ ያዘ (ቀለበት፥ ቀበቶ፥ ክር፥...)።

ክርክር ስ ተላላፊ የሆነ የአባለዘር በሽታ።

ክርክር (ክርክራት) ስ ለሙጥ በሆኑ ነገሮች ላይ የሚገኝ ብዙውን ጊዜ የቀለበት ቅርፅ ያለው የተገዘገዘ ወይም እንደ ሰንበር ያለ ምልክት።

ክርክሮሽ ዝ.ክ.

ተከረከረ ግ ክርክር አወጣ ወይም አበጀ።

አከረከረ ዝ.ክ.

***ከረከረ**

ክርክር ስ 1.በፍርድ ቤት ወይም በሸንጎ ላይ ከሳሽና ተከሳሽ የሚያደርጉት እሰጥ አገባ ወይም ሙግት። 2.በአንድ ጉዳይ ላይ የተለያየ አስተያየትና እምነት፥... ባላቸው ሰዎች መካከል አንዱ ሌላውን ለማሳመን የሚያደርጉት የንግግር ምልልስ ወይም እሰጥ አገባ። 3.በገዥና በሻጭ መካከል የሚደረግ የዋጋ ቀንስ አልቀንስም ንግግር።

ተከራከረ ግ 1. በፍርድ ቤት ወይም በሸንጎ

ላይ አንዱ ከሳሽ ሌላው ደግሞ ተከሳሽ ሆኖ ተሟገተ። 2. በአንድ ጉዳይ ላይ ከራሱ አስተያየትና እምነት፥... የተለየ አስተያየትና እምነት፥ ... ካለው ሰው ጋር (የራሱን እምነትና አስተያየት፥... እንዲቀበልለት ወይም እንዲረዳለት ለማድረግ) ሃሳብ ተለዋወጠ፥ ተጨቃጨቀ። 3. ዋጋ ቀንስ በማለት ገዢ ከሻጭ ጋር ተጨቃጨቀ።

አከራከረ ግ አወዛገበ፡ አጨቃጨቀ።

አከራካሪ ቅ አወዛጋቢ፥ አጨቃጫቂ።

ከረከሰ ግ 1.አረጀ። 2.ተንሳቀለ። 3.ክርካሳ ሆነ።

ክርካሳ ቅ አሮጌ፡ በሚገባና በተሟላ ሁኔታ መስራት የማይችል (ለምሳሌ መኪና)።

***ከረየ**

ኪራይ (ክራይ) ስ አንድ ተገልጋይ ለተወሰነ ጊዜ ለተገለገለበትና የራሱ ላልሆነ መገልገያ ነገር (እንደ እንስሳ፥ መኪና፥ ቤት፥ ቁሳቁስ፥... ላሉት) ለባለንብረቱ የሚከፍለው የጉልበት ወይም የአገልግሎት ዋጋ።

ተከራየ ግ 1.አንድን መገልገያ(ቤት፥ መኪና፥ ቁሳቁስ፥...) ኪራይ እየከፈለ ለመጠቀም ከባለንብረቱ ወሰደ ወይም ተረከበ። 2.መገልገያ የሆነው ነገር ለባለንብረቱ ኪራይ እየከፈለ ለሚጠቀም ተገልጋይ ተሰጠ።

ተከራይ (ኪራይተኛ) ስ ኪራዩን እየከፈለ የራሱ ባልሆነ ነገር የሚጠቀም ሰው።

አከራየ ግ ኪራይ እየከፈለ እንዲጠቀምበት መገልገያ ነገሮችን (ቤት፥ መኪና፥ ቁሳቁስ፥...) ለተገልጋዩ ሰጠ።

አከራይ ስ አንድን መገልገያ ለተከራይ እየሰጠ ኪራይ የሚቀበል ሰው።

ከረደደ ግ ደረቀ፥ ጠነከረ (ለምሳሌ ፀጉር)።

ክርዳዳ (ከረደድ፥ ክርድድ) ቅ ደረቅ፥ ጠንካራ፤ የለስላሳ ነገር ተቃራኒ።

ከረጢት ስ እንደ ከሮጆ ወይም እንደ ስልቻ ሆኖ ከጨርቃ ጨርቅ የሚሰፋ የእቃ መያዣ።

ከረሜ ስ እህል ውስጥ የሚገኝ ደቃቅ ድንጋይ፥ አሸዋ።

***ከረፈፈ**

ክርፋፋ (ከረፈፍ) ቅ 1.(ስድብ) ቅልጥፍና የሌለው፥ ጎታታ፥ ዘርፋፋ። 2.ልጥፍ ወይም ልስቅ የማይል፤ ጎርባባ።

ክርፍፍ አለ ግ ተንከረፈፈ።

ተንከረፈፈ ግ 1.ቅልጥፍና አጣ፥ ተጎተተ፥ ተንዘረፈፈ። 2.ተንጎረበበ፤ ልጥፍ ወይም ልስቅ ባይል ቀረ።

አንከረፈፈ ግ 1.ቀልጠፍ እንዳይል አደረገ፥ አንዘረፈፈ። 2.ልጥፍ ወይም ልስቅ ወይም ጠጋ እንዳይል አደረገ፤ አንጎረበበ።

እንክርፍ ቅ ክርፋፋ።

ከረፋ ግ ገማ፥ ጠነባ።

ክርፋት ስ ግማት፥ መጥፎ ሽታ።

ክርፋታም ቅ (ስድብ) ግማታም፥ ጥንባታም።

ከራራ "ከረረ" ስር ተመ.

ከሬ ስ 1.በቂጥ መጋጠሚያ ላይ የሚገኝ የአከርካሪ አጥንት። ቅ 2.በጣም የከሳ፥ አጥንቱ የገጠጠ።

ከርሞ "ከረመ" ስር ተመ.

ከርስ ስ ሆድ።

ከርሰ ሃመር ስ 1.የመርከብ ውስጠኛ አካል አማካይ ቦታ። 2.(ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) በመንበር ውስጥ የታቦት ማስቀመጫ ክፍል።

ከርሰ መቃብር ስ የመቃብር ውስጣዊ ክፍል።

ከርሰ ምድር ስ የመሬት ውስጠኛ ክፍል።

ከርሰ ፊደል ስ በያንዳንዱ የፊደል ቅርፅ ውስጥ የሚገኘውና ቀለም ያላረፈበት ክፍት ቦታ።

ከርሳም ቅ (ስድብ) 1.ሆዳም። 2.ቀፈታም።

ከርቤ ስ 1.ጥሩ ሽታ ያለውና እንደ እጣን የሚጤስ የዛፍ ሙጫ። 2.ከርቤ የተባለው ሙጫ የሚገኝበት ዛፍ።

ከርታታ "*ከረተተ" ስር ተመ.

ከርክሩሜ ስ ቅልጥሞቹ ረዥም የሆኑ፥ ቀንሙ ያለውና ምንቃሩ ትልቅ የሆነ የአሞራ አይነት።

ከርከሮ ስ 1.አሳማ የሚመስል፥ ጥርሱ ወጣ ያለና ቀንድ ያለው የዱር እንስሳ(ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።2.አጭርና ጉልበተኛ የሆነ ሰው።

ክርካሳ "ከረከሰ" ስር ተመ.

ከርክር "ከረከረ" ስር ተመ.

ክርዳዳ "ከረደደ" ስር ተመ.

ክርፋፋ "*ከረፈፈ" ስር ተመ.

ከሰለ ግ 1.ከነደደ በኋላ ወደ ከሰል ተለወጠ (እንጨት)። 2.አረረ፥ ጠቆረ፥ ከሰል መሰለ። 3.(ዘይ.) ተናደደ፥ በገነ፥ አረረ። 4.በከሰል ወይም በጥቁር ቀለም ፃፈ፥ ሳለ፥ ቀባ። 5.ሰረዘ (ፅሁፍን)።

ከሰል (ክሰል) ስ እንጨት ትንሽ አየር እንዲያገኝ ተደርጎ በዝግታ ከነደደና እንዲጠፋ ከተደረገ በኋላ ጥቁር ሆኖ የሚገኘው የእንጨቱ ክፍል፤ የከሰለ እንጨት።

ከሰሌ ስ ለከሰል የሚሆንና እሾክ የሌለው የግራር አይነት።

ከሰልማ ቅ የከሰል አይነት፥ ጥቁር።

ክስል ቅ የስርዝ ምልክት፥ እርማት የተደረገበት ፅሁፍ።

ክስል አክሳይ ቅ ክስል አምራች።

ከሰመ ግ 1.ኋሸሸ፥ ደረቀ፥ ረገፈ፥ ሻረ (የከፍኝ፥ የፈንጣጣ፥ የቂጥኝ ቁስል)። 2.ጠፋ።

ከሰረ ግ 1.ሸቀጡ ከተገዛበት ዋጋ ዝቅ ብሎ በመሸጡ ሻጩ ዋናውን ሳያገኝ ቀረ፥ ጎደለበት። 2.የፈለገውን ሳያገኝ ቀረ፥ አጣ። *ልጄን ላገኘዋለሁ ብዬ ሄጄ ከስሬ መጣሁ።*

ኪሳራ ስ 1.አንድ ሸቀጥ ከተገዛበት ዋጋ ዝቅ ብሎ በመሸጡ በዋናው ወይም በወረቱ ላይ የሚደርስ ጉድለት። 2.ያለመሳካት፥ የፈለጉትን ሳያገኙ መቅረት። 3.የቁማር ጨዋታ ዓይነት። 4.ወጪ። *ሁሉ ኪሳራ ተጓጓዝን።*

ኪሳራ ነው ትርፍ የለውም።

ኪሳራ ውስጥ ገባ ከሰረ።

ክስረት ስ የ"ኪሳራ"ን 1ኛ ፍቺ ተመ.።

አከሰረ ግ 1.ዋናውን ሳይመልስ ቀረ፥ አጎደለ (ሸቀጥ)። 2.እንዲጠፋ ወይም እንዲባክን ምክንያት ሆነ።

አክሳሪ ቅ 1.ብዙ ወጪ የሚያስወጣ። 2.ትርፍ የማያስገኝ። *አክሳሪ ድርጅት።*

ከሰሰ ግ 1.የደረሰበትን በደል ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ አካል አመለከተ፥ አቤቱታ አቀረበ። 2.አጋለጠ፥ ወነጀለ፥ አሳጣ። 3.በዳይን ወይም ወንጀለኛን ከህግ ፊት አቀረበ።

ከሳሽ ስ ወንጀልን ወይም በደልን አስመልክቶ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ አካል በፅሁፍ ወይም በቃል አቤቱታ አቅራቢ።

ክስ ስ ወንጀልን ወይም በደልን አስመልክቶ በፅሁፍ ወይም በቃል የሚቀርብ አቤቱታ።

ተከሰሰ ግ ክስ ቀረበበት፥ ተወነጀለ።

ተከሳሽ ስ ጥፋተኛ ነው ተብሎ ክስ ወይም አቤቱታ የቀረበበት ሰው።

ተካሰሰ ግ ከሳሽ ወይም ተከሳሽ በመሆን ህግ ፊት ቀረበ።

ተካሰሱ ግ አንዱ ከሳሽ ሌላው ተከሳሽ በመሆን ህግ ፊት ቀረቡ።

አካሰሰ ግ ለክስ ምክንያት ሆነ።

ከሰተ ግ ገለጠ፥ እንዲታወቅ አደረገ።

ከሰተበት ተጋለጠ፥ ታወቀበት።

ክስተት ስ 1.ሊዳሰስ፥ ሊሸተት፥ ሊሰማ ወይም ሊታይ የሚችል ማንኛውም ነገር። 2.መገለጥ፥ መታየት።

ተከሰተ ግ ታየ፥ ተገለጠ።

ከሰከሰ ግ 1.ሰባበረ፥ አደቀቀ። 2.ፈነከተ፥ ፈለጠ፥ መታ (በዱላ፥ በድንጋይ)። 3.ብዙ ገንዘብ አፈሰሰ፥ አወጣ፥ አጠፋ። 4.አብዝቶ በብዛት አስቀመጠ፥ ቸመቸመ። 5.በብዛት አደረገ፥ ፈፀመ (መብላትን፥ መስራትን፥ ...)።

ክስካሽ ቅ ስባርባሪ።

ክስክስ ቅ ተጠጋግቶ ወይም ተቀራርቦ በብዛት የተቀመጠ፥ ድርድር።

ተከሰከሰ ግ 1.ወድቆ ተሰበረ። 2. በሃይል ወደቀ፥ ፈረጠ።

ተካሰከሰ ግ ተፈናከተ፥ ተደባደበ።

አከሰከሰ ግ በብዛት አበላ፥ አጠጣ፥ ...።

አካሰከሰ ግ ለመደባደብ ወይም ለመፈናከት ምክንያት ሆነ።

ከሳ ግ ቀጠነ፥ የሰውነቱ ውፍረት ቀነሰ፥ ሞገገ።

ከሲታ ቅ ኮስማና፥ ሞጋጋ።

ክሳት ስ ቅጥነት፥ የውፍረት ተቃራኒ።

ከሳሽ "ከሰሰ" ስር ተመ.

ከሴ ስ ቅጠሉ ሻካራ ሆኖ ጥሩ ሽታ ያለው የእፅዋት አይነት።

ከስከሶ ስ ቅጠሉ ሰሳሳ ሆኖ ነጣ ያለ፥ ጥሩ ሽታ ያለውና ችምችም ብሎ የሚበቅል የቁጥቋጦ አይነት።

ከሸለለ (ኮሸለለ) ግ ኳ ብሎ ደረቀ።

ከሸሌል (ኮሸላላ) ቅ ደረቅ።

ከሸነ ግ 1.አሳምሮ ሰራ። 2.አጣፍጦ ሰራ (ወጥን)።

ክሽን ቅ የሚያምር፥ ዝይን።

ተከሸነ ግ አማረ፥ ተዋበ።

ከሸከሸ ግ ኩርሽም ኩርሽም ወይም ከሽ ከሽ እያደረገ አኘከ፥ በላ (ለምሳሌ የደረቀ እንጀራን)።

ክሽክሼ ስ ሲበሉት ከሽ ከሽ የሚል ድምፅ የሚሰጥ በፀሃይ ወይም በሰማ ምጣድ ተንቃቅቶ የደረቀ እንጀራ።

ከሸፈ ግ 1.ተሰናከለ፥ ተጨናጎለ፥ ሳይሳካ ቀረ። 2.አልተኮሰ አለ (ጥይት)።

ከሽ

ከሽ አለ ግ እንደ ሸክላ እቃ፥ ጠርሙስ፥ ... ያለ ነገር ወድቆ ተሰበረ ወይም የተጠቀሱት እቃዎች ወድቀው ሲሰበሩ የሚሰጡት አይነት ድምፅ ሰጠ።

ከሽ ከሽ አለ ግ (እንደ ቆሬያ፥ ድርቆሽ፥... ያለ ነገር) ሲያኝኩት ኩርሽም ኩርሽም የሚል ድምፅ ሰጠ።

ከሽከሼ "ከሸከሸ" ስር ተመ.

***ከበለለ**

ከብለል ከብለል አለ ግ ደብለል ደብለል አለ፥ ተገላበጠ።

ክብልል አለ ግ ተንከባለለ።

ተንከባለለ ግ 1.መሬት፥ አልጋ፥... ላይ ወዲያ ወዲህ ተገላበጠ። 2.እየተንደባለለ ቁልቁል ወረደ።

አንከባለለ ግ 1.አንደባለለ። 2.እየተንደባለለ ቁልቁል እንዲሄድ ወይም እንዲወርድ አደረገ።

እንክብል ስ 1.ክብና ድቡልቡል የሆነ ነገር። 2.ኪኒን።

ከበረ ግ 1.ባለፀጋ ወይም ሃብታም ሆነ። 2.ክብር፥ አክብሮት፥ ማእረግ አገኘ።

ከበሬታ ስ ክብር፥ ማእረግ።

ከበርቴ ስ ሃብታም ወይም ባለፀጋ።

ክቡር በፊደል ተራው ተመ.

ክብረት ስ ክብር።

ክብር ስ 1.ማእረግ፥ ወግ። 2.ልእልና፥ ገናናነት፥ ታዋቂነት።

ክብሩን ጠበቀ 1.ክብሩ እንዳይደፈር አደረገ። 2.በጨዋነት ተገኘ።

ክብሯን ጠበቀች ድንግልናዋን ሳታጣ ባል እስከምታገባ ድረስ ቆየች።

ክብረ ሰማይ ስ ሰዎች ለቁስል መድሃኒት ይሆናል ብለው የሚጠቀሙበት የማእድን አይነት።

ክብረ በኣል ስ በየአመቱ የሚከበር ትልቅ መንፈሳዊ በኣል።

ክብረ ነክ የአንድን ግለሰብ ወይም አካል ክብር የሚያጎድፍ፥ የሚያንቋሽሽ (ነገር፥ ሁኔታ፥ ...)።

ክብረ ነገስት ስ በንቡረእድ ይስሃቅ የተዘጋጀ የነገስታት ታሪክ መፅሃፍ።

ክብረ ንፅህና ስ ድንግልና፤ የግብረ ስጋ ግንኙነት ፈፅሞ ያለማወቅ ሁኔታ (ለሴት)።

ክብረ ወሰን ስ ብዙውን ጊዜ በስፖርታዊ ውድድር ላይ አዲስ የሚገኝና ከዚህ በፊት በሌላ ተወዳዳሪ ያልተደረሰበት ከፍተኛ የውጤት እርከን፤ ሪኮርድ።

የክብር መዝገብ ስ ኤግዚቢሽን፥ትርኢት ጎብኚዎች ስለተመለከቱት ነገር ያላቸውን አስተያየት እንዲያሰፍሩበት በኤግዚቢሽኑ ቦታ የሚቀመጥ ወይም በኤምባሲ ወይም በቆንስላ ፅቤቶች ውስጥ ለሃዘን ጊዜ የየአገሩ መሪዎች ወይም ትልልቅ ባለስልጣናት ሃዘናቸውን ገልፀው እንዲፅፉበት የሚዘጋጅ መዝገብ።

የክብር ተከታይ ስ አንድ ርእሰ ብሄር ከራሱ አገር ውጪ በሚሄድበት ጊዜ አብሮት የሚሄድ አጃቢ፥ ባለሟል።

የክብር እንግዳ ስ እንደ ግብዣ፥ ስብሰባ ባሉ ዝግጅቶች ላይ ከሌሎች ተጋባዥ እንግዶች በተለየ ሁኔታ ጥሪ ተደርጎለት የሚገኝ እንግዳ።

የክብር ዘብ ስ አንድን ታላቅ ባለስልጣን ለማጀብ ወይም ለመጠበቅ የተመደበ ወታደራዊ ጓድ።

ክብርና ስ ድንግልና፤ ክብረ ንፅህና።

ተከበረ ግ 1.ክብር አገኘ ወይም ተሰጠው። 2.ታፈረ፥ ተፈራ። 3.እንዳይነካ ተደረገ፥ ተከለከለ፤ ተጠበቀ (ሃብት፥ ንብረት)። 4.አንድን በኣል በሚመለከት ተገቢው ስነስርአት ተካሄደ።

አከበረ ግ 1.አላቀ፥ ከፍ አደረገ፤ ወግ ማእረግ ሰጠ። 2.ከበሬታ ሰጠ፤ በትህትና አስተናገደ። 3.በኣል አደረገ፤ በበኣሉ ምክንያት አረፈ ወይም ስራ ሳይሰራ ዋለ። 4.በበኣሉ ስነስርአት ላይ ተሳታፊ ሆነ።

አስከበረ ግ 1.በህግ አስጠበቀ፥ አስከለከለ፥ እንዳይነካ አስደረገ (ንብረትን)። 2.እንዳይደፈር አደረገ ወይም አስደረገ (አገርን፥ ወገንን፥ ...)።

ከበሮ (ከረቦ) ስ አብዛኛውን ጊዜ የሾላ፥ የኮርች፥... ግንድ ጉማጅ ከኣፉ ሰፋ ከቂጡ ጠበብ ያለ ቅርፅ እንዲይዝ ተደርጎ ውስጡ ከተቦረቦረ በኋላ አፍና ቂጡ ላይ ቆዳ ተወጥሮ የሚሰራና በእጅ ሲመቱት ድምፅ የሚሰጥ የሙዚቃ መሳሪያ። (ነጋሪትን፥ አታሞን፥ ድቤን ተመ.)(ስእሉን የሙዚቃ መሳሪያ ስር ተመ.)።

ከበሮ ቤት ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) በቅኔ ማህሌትና በአምደ ወርቅ ግራና ቀኝ የሚገኝ በማህሌት ጊዜ ተማሪዎች የሚቆሙበት ቦታ።

ከበሰ ግ 1.ጠመጠመ፥ ደገሰለ (ሻሽን)። 2.አሳበጠ፥ አድበለበለ (እግርን)። 3.ክባስ አበጀ።

ክባስ ስ 1.ቄሶች ራሳቸው ላይ የሚጠመጥሙት ትልቅ ጥምጥም። 2.በወጋግራ ጫፍ ላይ የሚሰካና ጣሪያ ተሸካሚ የሆነው አግዳሚ ማእዘን የሚያርፍበት ሞላላ ቅርፅ ያለው አጭር እንጨት።



ክባስ 1ኛ ፍቺ

*ከበሰበሰ

ክብስብስ ቅ ዘርፋፋ፥ ጎታታ (በአለባበስ፥ በአካሄድ)።

ተክበሰበሰ ግ ሰፊና ረጅም ልብስ ለብሶ እየተግበሰበሰ በዝግታ ተራመደ፥ ተጎተተ።

አክበሰበሰ ግ አንዘረፈፈ፥ ጎተተ (ልብሱን)።

ከበበ ግ 1.ክብ ሰራ። 2.ዙሪያውን ያዘ። *ከተማውን ከበውታል።* 3.አንድን ነገር መሃል በማድረግ ዙሪያውን ሆነ። *ዘፋኙን ከበው ይጨፍራሉ።* 4.ዙሪያውን አደረገ። *በውሃው ጉድጓድ ውስጥ ቆሻሻ እንዳይገባበት ዙሪያውን*

በድንጋይ ከበበው። 4.አጀበ፥ ተከተለ፤ አብሮ ሆነ።

ከበባ ስ አንድን ቦታ ወይም ጠላትን፤... በዙሪያ የመ ከበብና የመቆጣጠር ድርጊት።

ከበባ አደረገ ግ አንድን ነገር ለመያዝ ወይም ለማ ጥቃት ወይም ለመውረር ከበበ።

ከባቢ አየር ስ በመሬት ዙሪያ ያለ አየር።

ከባቢ ጦር ስ የጠላትን ጦር መሃል አድርጎ ዙሪያውን በመከበብ የሚዋጋ ጦር።

ከባባ ስ የመቅረዝ መብራትን ለማጥፋት በመቅረዙ ላይ የሚደፉ መስኪያ የሚመስል እቃ።

ክበብ ስ 1.ለአንድ አይነት አላማ ወይም ማህበራዊ ጉዳይ ሰዎች የሚሰባሰቡበት ቡድን ወይም ድርጅት። 2.መዝናኛ ቦታ (ብዙውን ጊዜ መስሪያ ቤት አካባቢ)። 3.ዙሪያ።

ክብ ቅ 1.እንደቀለበት ዙሪያነት ያለው (አካል፥ ቅርፅ)። 2.ድቡልቡል፥ እንክብል።

አከበበ ግ ክብ ሰራ።

አካበበ ግ አዋሰነ፥ ወሰንተኛ ሆነ፥ አካለለ።

አካባቢ ስ 1.ሰፈር፥ ቀበሌ፥ ቦታ። 2.የአንድ ነገር ዙሪያ፥ ጅክክ፥ አጠገብ፥ አቅራቢያ። 3.ገደማ(ለጊዜ)። *አሰራ ሁለት ሰዓት አካባቢ አገኘኝ*።

***ከበከበ**^{1}

ተንከባከበ (ተከባከበ) ግ 1.በድሎት ወይም በምቾት ያዘ፥ አቀማጠለ። 2.በጥንቃቄ ያዘ።

አንከባከበ ግ ተንከባከበ።

እንክብካቤ (ክብካቤ) ስ 1.መልካም አያያዝ። 2.ምቾት፥ ድሎት።

እንክብክብ ቅ በምቾት ወይም በድሎት የተያዘ፥ ቅምጥል።

***ከበከበ**^{2}

አንከበከበ ግ 1.አድበለበለ፥ እንደ ኳስ አደረገ። 2.ብቀላሉ ብድግ አድርጎ ተሸከመ።

እንክብክብ ቅ ድቡልቡል።

ከበደ ግ 1.መዘነ፥ በዛ (ሸክም)። 2.አቃተ፥ በረታ፥ አስቸገረ። *ፈተና ከበደ / ኑሮ ከበደ*። 3.ተጫጫነ። *ራሴን ከበደኝ*። 4.ቀፈፈ። *ቀን ከበደኝ*። 5.ታፈረ፥ ተፈራ፥ ተከበረ።

ከበደች አረገዘች (ላም፥ ፈረስ፥...)።

ከባድ ቅ 1.ክብደት ያለው፥ ቀላል ያልሆነ። 2.ትልቅ። 3.ብርቱ፥ ጠንካራ። 4.አስቸጋሪ፥ አዳጋች። 5.አስፈሪ። 6.ጎበዝ፥ ሃይለኛ። *ከባድ ኳስ ተጫዋች ነው*። 7.ከፍተኛ። *ከባድ ወጪ የሚጠይቅ ስራ*።

ከባድ መሬት ስ ጥቁር አፈር፥ መረሬ።

ከባድ ሚዛን ቅ ከፍተኛ ክብደት ያለው። *የከባድ ሚዛን ቦክሰኛ*።

ከባድ ምግብ ስ ጨጓራ በቀላሉ ሊፈጨው የማይችለው ምግብ።

ከባድ ኢንዱስትሪ ስ ማምረቻ መሳሪያዎችን የሚያመርት ኢንዱስትሪ።

ክበድ ቅ እርጉዝ (እንስሳ)።

ክብደት ስ 1.የመመዘን፥ የመክበድ ሃይል። 2.አስቸጋሪነት፥ አዳጋችነት። 3.ከፍተኛነት፥ አስፈላጊነት። *የጉዳዩን ክብደት አይተው አስቸኳይ ስብሰባ ጠሩ*። 4.ትኩረት፥ ትልቅ ግምት። *ለነገሩ ክብደት አልሰጠውም*።

ክብደት ያንሳል ሰውነቱን ለማዳበርና ለማጠንከር እንዲሁም ለስፖርታዊ እንቅስቃሴ ተብሎ የተዘጋጀ ድንጋይ ወይም ብረት በእጆቹ ወደላይ በማንሳትና በማስቀመጥ ስፖርታዊ እንቅስቃሴ ያደርጋል።

ክብደት አንሺ ስ ሰውነቱን ለማዳበርና ለማጠንከር ክብደት ያለውና ለዚሁ ስፖርታዊ እንቅስቃሴ ተብሎ የተዘጋጀ ድንጋይ ወይም ብረት በእጆቹ ወደላይ በማንሳትና በማስቀመጥ ስፖርታዊ እንቅስቃሴ የሚያደርግ ሰው።

ተካበደ ግ ከበደ።

አከበደ ግ አጋነነ፥ ትልቅ ቦታ ሰጠ። *በቀላሉ ሊያልቅ የሚችለውን ጉዳይ አከብደህ አትየው*።

ከባቢ "**ከበበ**" ስር ተመ.

ከባባ ገ.ከ.

ከባድ "**ከበደ**" ስር ተመ.

ከብት ስ 1.እንደ ላም፥ ፈረስ፥ በግ፥... ያሉ የቤት እንስሳት በጥቅል የሚጠሩበት ስም። 2.በሬ ወይም ላም። 3.(ለድብ፥ ዘይ.) ሞኝ፥ ጅል።

ከብት ነጂ ስ 1.የከብት ሌባ ወይም ዘራፊ። 2.ከብት የሚጠብቅና የሚያጓጉዝ የከብት ነጋዴ ተቀጣሪ።

ከብት አርቢ ስ መተዳደሪያው ከብት ማርባት ላይ የተመሰረተ (ሰው)።

የከብት ሃኪም ስ የእንስሳት ሃኪም።

የከብት ዝምብ ስ ትልቅ የሆነ ዝምብ።

***ከተለ**

ምክትል ስ ለአንድ ባለስልጣን የቅርብ ተተኪ ወይም የበታች ባለስልጣን ወይም በማእረግ (በደረጃ) ሁለተኛው የሆነ ሰው። *ምክትል ስራ አስኪያጅ*።

ክተል አለ ግ ወዲያውኑ ተከተለ።

ክተል አደረገ ግ ቀጠል አደረገ፥ አስከተለ።

ተከተለ ግ 1.ለጠቀ፥ ቀጠለ። 2.ከአንድ ነገር

ሄላ ሄላ ሄደ። 3.በሌላው ተመራ። 4.አመነ፣ ተቀበለ (የሌላውን መሪነት፣ ሃሳብ፣...)።

ተከታይ ቅ 1.ሰባቂ፣ ቀጣይ። 2.አጃቢ ወይም አብሮ ሂያጅ። 3.አማኝ። *የክርስትና ሃይማኖት ተከታይ።* 4.ከታላቁ ቀጥሎ የተወለደ፣ ታናሽ (በእድሜ)። *የእኔ ተከታይ ሴት ናት።*

ተከታተለ ግ 1.አንዱ ከሌላው ቀጠለ ወይም አንዱ ሌላውን ተከተለ። 2.በትጋት ወይም በንቃት ተመለከተ፣ ተቆጣጠረ፣ ተጠባበቀ፣ አጠና። 3.አሳደደ። *ተከታተሉት ያዙው።*

ተከታታይ ቅ 1.ሳያቋርጥ አንዱ ከሌላው የሚቀጥል። 2.ታላቅና ታናሽ የሆኑ (ሰዎች)። 3.ጉዳይ አስፈፃሚ።

አከታተለ ግ 1.አንዱን ከሌላው ቀጠለ። 2.ወዲያውኑ ቀጠለ። *እሱን ካነጋገረች በኋላ አከታትላ ለኔ ደወለች።* 3.ደጋገመ። *አከታትለው ሰባት ብርጭቆ ውሃ ጠጣ።*

አስከተለ ግ 1.ተከታይ አደረገ። 2.አንድ ነገር ከሌላው ነገር ቀጥሎ እንዲሄድ ወይም እንዲመጣ አደረገ።

አስከታይ ቅ የተከታይን 5ኛ ፍቺ ተመ.

ከተለበ ግ ሞጨለፈ፣ ነጥቆ ሮጠ።

***ከተለበ**

ክትላብ ቅ ክላብ።

ተከታለበ ግ ተካለበ።

አከታለበ ግ አካለበ።

ከተለፈ ግ ሞጨለፈ፣ ነጥቆ ሮጠ።

ክትላፋ ቅ (ስድብ) 1.ሞጭላፋ። 2.ክላፋ፣ ቀዥቃዣ።

ከተመ¹ ግ 1.ከተማ ቆረቆረ ወይም መሰረተ። 2.ተሰበሰበ፣ ተከማቸ፣ ሰፈረ፣ በአንድነት ኖረ (ህዝብ)።

ከተማ ስ ከግብርና በስተቀር በሌሎች ሙያዎች የሚተዳደሩ በርካታ ሰዎች በተጠጋጉ ቤቶች ውስጥ የሚኖሩበት፣ ድርጅቶችና የመንግስት መስሪያ ቤቶች የሚገኙበት ቦታ፣ ሰፈራ፣ አካባቢ።

ከተማ ቀመስ ገጠር ሆኖ በአንዳንድ ሁኔታዎች ከከተማ ጋር የሚመሳሰል ቦታ ወይም ገጠሬ ሆኖ አንዳንድ የከተሜ ባህርይ የሚታይበት ሰው።

የከተማ ልጅ ስልጡን፣ ሙሌ።

ከተሜ ስ የከተማ ሰው።

ተከታተመ ግ አንዱ ለአንዱ ወይም ጎን ለጎን በመሆን ድንኳን ተከለ፣ ሰፈር አደረገ (ዘማች፣ ጦር ሰራዊት)።

ከተመ² ግ የተፈላው ቡና ከአንደኛ እስከ ሶስተኛ ተጠጥቶ አለቀ።

አከተመ ግ 1.የተፈላውን ቡና ከአንደኛ እስከ ሶስተኛ (አቦል፣ ቶናና በረካውን) ጠጥቶ ጨረሰ። 2.አበቃ፣ አለቀ፣ ተፈፀመ።

ከተማ "**ከተመ¹**" ስር ተመ.

ከተሜ ገ.ከ.

ከተረ ግ 1.ከመሄድ ታገደ፣ ቆመ፣ ረጋ (ለምሳሌ ውሃ)። 2.እንዳይሄድ ገደበ፣ ከለከለ፣ አቆመ (ለምሳሌ ውሃን)።

ከተራ ስ ለመጠመቂያ እንዲያገለግሉ ወንዞች የሚጠረጉበትና የሚገደቡበት ቀን፤ የጥምቀት ዋዜማ።

ክትር ቅ ግድብ፣ እግድ።

ከተበ¹ ግ ፃፈ።

ክታብ ስ 1.ከበሽታ እንዲያድን ወይም ከክፉ ነገር እንዲጠብቅ ተብሎ በብራና ወይም በወረቀት ላይ ተፅፎና ተጠቅልሎ በአንገት ወይም በክንድ ላይ የሚታሰር መድሃኒት። 2.በቆዳ ወይም በጨርቅ ተጠቅልሎ አንገት ወይም ክንድ ላይ የሚታሰር የስራ-ስር መድሃኒት።

ከተበ² ግ ክትባት ሰጠ ወይም አደረገ።

ክትባት ስ በሽታን እንዲከላከል በመርፌ ወይም ሰውነትን በመብጣት የሚሰጥ መድሃኒት።

ተከተበ ግ ክትባት ወሰደ ወይም ተደረገለት።

ከተተ ግ 1.ዶለ፣ ጨመረ፣ አገባ፣ አስገባ። 2.አስቀመጠ፣ አኖረ። *ገንዘቡን ባንክ ቤት ከተተ።* 3.ሰበሰበ (አዝመራን)። 4.ቻለ፣ ያዘ፣ በቃ። *ይህን ሁሉ ልብስ ሻንጣው አይከተውም።* 5.ተሰበሰበ፣ አበረ። *ረዥም የነበረው ቀሚስ ቢታጠብ ከተተ።* 6.ዋጠ። *ድመቷ ትልቋን አይጥ እንዳለች ከተተቻት።* 7.ተጠቃሎ ተሰበሰበ፣ አንድ ቦታ ተከማቸ። *ለቀጃ ከተነገረ በኋላ ሰራዊቱ ከተተ።*

ክታች ስ አዝመራ ተሰብስቦ የሚያበቃበት ወቅት።

ክት ቅ 1.እጥር ምጥን ያለ። 2.ቁጥብ፣ አመለ ሰብሰብ።

የክት ቅ የዘወትር ያልሆነ።

የክት ልብስ ስ ለበአል የሚለበስ ልብስ፣ የሰርክ ልብስ ያልሆነ።

ክትት አለ ግ ወዲያ ወዲህ ማለት ወይም መዞር ተወ፣ ተሰበሰበ። *እሱ በጣም ጨዋ ነው በጊዜ ቤቱ ክትት ይላል።*

ተከተተ ግ 1.ክትት አለ። 2.ተፈፀመ፣ አበቃ። *የእነሱ ነገር አበቃ ተከተተ።*

ተካተተ ግ 1. ተጠቃለለ። 2. ተጠናቀቀ። 3. ተጨመረ፣ ታከለ።

መካተቻ ስ ማለቂያ፣ መደምደሚያ፣ ፍፃሜ።

አካተተ ግ 1. አጠቃለለ፣ አጠቃሎ ያዘ። 2.

አጠናቀቀ፥ ጨረሰ፥ ፈፀመ። 3. ጨመረ፤ አከለ(ቀድሞ በነበረው ላይ)።

ከተከተ ግ በአጭር በአጭሩ ወይም በትንሽ በትንሹ ቈረጠ፣ ቈራረጠ፣ ሸነሸነ። 2.ጨፈጨፈ፣ ቈረጠ። 3.ቈረጠመ፥ ገተገተ (ህመም ሰውነትን)።

ክትካች ቅ ቁርጥራጭ፥ ስብርባሪ (የእንጨት)።

ተከታከተ ግ አንዱ ከሌላው ጋር ተማታ፣ ተቀጣቀጠ፥ ተደባደበ (በዱላ)።

አከታከተ ግ ለመደባደብ ምክንያት ሆነ።

***ክትክት**

ክት ብሎ ሳቀ በጣም ሳቀ።

ክትክት አለ ግ ተንከተከተ።

ክትክት ብሎ ሳቀ ዝ.ክ.

ተንከተከተ ግ በጣም ሳቀ፣ ተንፈቀፈቀ።

አንከተከተ ግ በጣም አሳቀ፥ አንፈቀፈቀ።

ከተፈ ግ በትንንሹ መተረ፤ ቈረጠ፣ ሸነሸነ።

መክተፊያ ስ እንደ ሽንኩርት፣ ስጋ፣... ያሉ ነገሮችን ለመቆራረጥ ወይም ለመክተፍ የሚያገለግል ዝርግ እንጨት ወይም ሌላ ነገር።

ክትፎ ስ ቅቤና ሚጥሚጣ ተጨምሮበት ብዙውን ጊዜ ጥሬውን እንዲበላ ሆኖ የሚዘጋጅ ድቅቅ ብሎ የተከተፈ ብርንዶ ስጋ።

ክትፎ ለብለብ ስ በመጠኑ ወይም በጣም ሳይበስል የተጠበሰ ክትፎ።

***ከተፈ**

ክተፎ ቅ ፈጣን።

ክተፍ አለ ግ ክች አለ፣ በድንገት መጣ ወይም ደረሰ።

ክትፍትፍ ቅ 1.ፈጣን። 2.ቀልጣፋ።

ተክተፈተፈ ግ 1.ተቅለበለበ፣ ተንቀዠቀዠ። 2.ተጣደፈ፣ ተቻኮለ።

አክተፈተፈ ግ አጣደፈ፥ አቻኮለ።

ክትላባ "*ከተለበ" ስር ተመ.

ክትላፋ "ከተለፈ" ስር ተመ.

ከቶ 1.ጭራሽ፣ ፈፅሞ። 2.እረ፣ እንዲያው ለመሆኑ።

ከቶውንም ተው. ግ. ጭራሹንም፥ ይብሱንም፥ ይልቁንም።

ከቸረ (ኮቸረ) ግ ደረቀ፥ ከቸቸ።

ከቸሮ ቅ ለዛ ቢስ፣ ደረቅ፥ ችኮ።

ኮቸሮ ስ 1.የደረቀ እንጀራ። 2.ለስንቅ እንዲሆን ተብሎ ከስንዴ፣ ዱቄት፥... እንደ ብስኩት ሆኖ የሚዘጋጅ ደረቅ ምግብ።

ከቸቸ ግ 1.ደረቀ፥ ወዝ አጣ። 2.ለዛ አጣ፥ ችኮ ሆነ።

ከቻቻ (ክቾ) ቅ 1. ደረቅ። 2.ለዛቢስ፣ ችኮ።

ክችች አለ ግ 1.ድርቅ አለ። 2.ክው አለ (በድንጋጤ)። 3. ሙግግ አለ፥ ችኮ ሆነ።

***ከቸቸ**

ከቸች አለ ግ ከተፍ አለ፥ ድንገት መጣ ወይም ደረሰ።

ክች አለ ዝ.ክ.

ከቻቻ "ከቸቸ" ስር ተመ.

ከነ___ (ከእነ___) መዋ. ___ጋር፥ ___ጭምር፥ ___ሳይቀር። *ሊቀየዋ ከነልጇ ተሸልማ ነበር /ልጇን ለይቼ ላላውቀውም ከነመልኩ ጠፍቶኛል።*

***ከነበ**

ክንብንብ ስ ነጠላ፣ ጋቢ፣... ሲለበስ ጭንቅላት ላይ የሚያርፈው የልብሱ ክፍል።

ክንብንብ አለ ግ ተከናነበ።

ተከናነበ ግ እንደ ጋቢ፥ ነጠላ፣... ባሉ ልብሶች (ብዙውን ጊዜ አይኑ አካባቢ ያለው የፊቱ ክፍል ሲቀር) ጭንቅላቱን፥ ማጅራቱን፥ ... ጭምር ሸፈነ።

አከናነበ ግ በልብስ ሸፈነ ወይም ሸፋፈነ።

አከናነበው አሸከመው (ስድብን)፣ ፈረደበት (ፍርድን)፣ ቀለለበት፣ ጫነበት (እዳን)።

ከነበለ ግ 1.ቸለሰ፣ አፈሰሰ። 2.ገለበጠ፣ ደፋ። 3.ጣለ፣ ፈነገለ።

ከንባላ ቅ በቂጡ ቅርፅ የተነሳ መሬት ላይ ተደላድሎ መቀመጥ የማይችል፣ ፍንግል የሚል (እቃ)።

ተከነበለ ግ 1.ፈሰሰ። 2.ተገለበጠ፣ ተደፋ። 3.ወደቀ።

ከነተረ ግ በሃይል መታ፣ ጣለ፣ አፈረጠ።

ከንተሮ ስ 1.በአንደኛው ጫፉ ላይ ጉልጥምት ወይም ቋር ያለው አጭር ዱላ። ቅ 2.አጭር ሆኖ ፈርጠምና ጠንከር ያለ (ሰው)።

ክንትር ስ አጣድፎ የሚገድል በሽታ።

ክንትር አለ ግ 1.ፍንችር አለ። 2.ወዲያው ወይም ከመቅፅበት ሞተ።

ከነቸረ ግ 1.ቀንጠረ፣ ደረቀ፣ ደበነ። 2.አጭርና ቀጭን ሆኖ ጠንከረ፣ ከረረ። 3.ቀፍድዶ ወይም ጠርንቆ አሰረ። 4.በሃይል ወርውሮ ጣለ፥ ዘረረ፣ ፈነቸረ።

ክንችር አለ ግ 1.ወደቀ፣ ተዘረረ፥ ተፈነቸረ። 2.ወዲያው ወይም ከመቅፅበት ሞተ።

ተከነቸረ ግ ተፈነቸረ፣ ወደቀ።

ከነአካቴው "ከናካቴው"ን ተመ.

ከነከታቴው ዝ.ክ.

ከነከነ ግ 1.ከረከረ፣ ሰረሰረ (ጉሮሮን)።

2.ቆረቆረ፡ አሳሰበ (ነገር)። 3.ፀፀተ፥ ቆጨ።

*ከነወነ

ክንውን ስ 1.ድርጊት፥ ተግባር። 2.አሰራር፥ አፈፃፀም።

ክንዋኔ ዝ.ክ.

ተከናወነ ግ 1.ተሰራ። 2.ተጠናቀቀ ወይም ተፈፀመ። 3.ተሳካ፡ ሰመረ።

አከናወነ ግ 1.ሰራ። 2.አጠናቀቀ፡ ፈፀመ፡ ጨረሰ። 3.አሳካ፡ አሰመረ።

ከነዳ ግ 1.በክንድ ለካ። 2.ከዳኛ ዘንድ እንዲቀርብ የተወሰነበት ሰው ሳይቀርብ በመቅረቱ ተቀጣ፡ ኪሳራ ከፈለ (የቆየ አጠቃቀም)። 3.በአጠፌታ ከፈለ (ካሳን፡ መቀጫን)።

ክናድ ስ የልብስ እጅጌ።

ክንድ ስ 1.ከእጅ ጣት እስከ ትከሻ ያለው የሰውነት ክፍል። 2.ከክርን እስከ እጅ ጣት ያለው የእጅ ክፍል። 3.ርዝመቱ ከክርን እስከ እጅ ጣት መጨረሻ የሚደርስ የርዝመት መለኪያ(ስእሉን ሰውነት ስር ተመ.)።

ክንዴ ነው አጋሬ፡ ደጋፊዬ፡ ረዳቴ ነው።

ክንዴን ሳልንተራስ ሳልሞት ወይም በህይወት እያለሁ።

ክንድ አከለ አፈረ ወይም ኩምሽሽ አለ።

ክንድ ያህላል 1.ትልቅ ነው (ለሙዝ፡ ለበቆሎ)። 2.በጣም አጭር ነው (ለሰው)።

ክንድህን አሳይ ሃይልህን፡ጉልበትህን አሳይ።

ክንድህን አንሳ በህብረት፡በአንድነት ተዋጋ፡ ተፋለም፥ ተከላከል።

ክንድህን አውሰኝ ምታልኝ፥ ደብድብልኝ።

አስከነዳ ግ 1.አስከፈለ (እዳን)። 2.በለጠ፡ ረታ፡ ላቀ። *ለጊዜ ለጊዜን በችሎታ ያስከነዳዋል።*

ከነፈ ግ 1.በረረ (በክንፍ)። 2.በከፍተኛ ፍጥነት ሮጠ፥ በነነ። 3.ተዋከበ፥ ተቻኮለ፥ ተራወጠ። 4.የሚያደርገውን አጣ፡ አበደ (በፍቅር፥ በደስታ፡...)።

ክንፍ ስ በወፍ፡ በዝንብ፥... ጎን ግራና ቀኝ ላይ የሚገኝ በአየር ላይ እየተንሳፈፉ ለመብረር የሚያስችል የአካል ክፍል።

ክንፍ

ክንፉን ዘረጋ በከፍተኛ ፍጥነት ሮጠ፡ በነነ።

ተከነፈነፈ ግ ተከለፈለፈ፡ ተንቀዠቀዠ።

አከነፈነፈ ግ አከለፈለፈ፡ አንቀዠቀዠ።

*ከነፈሰ

አከነፈሰ ግ አሸረገደ፥ አጎበጎበ።

አከንፋሽ ቅ አሸርጋጅ፥ አጎብጓቢ።

ከናካቴው (**ከነከታቴው፥ ከነአካቴው**) ይባስ ብሎ፥ ከነጭራሹ። *ሊቃው ተበላሽ በገል ከናካቴው ጠፋ።*

ከናፍር "**ከንፈር**"ን ተመ.

ከንባላ "**ከነበለ**" ስር ተመ.

ከንተሮ "**ከነተረ**" ስር ተመ.

ከንቱ ቅ ብላሽ፡ የማይረባ፡ ጥቅም የሌለው፡ ዋጋ ቢስ።

ከንቲባ ስ በማዘጋጃ ቤት አስተዳደር ዋናው የከተማ ሹም።

ከንትር "**ከነተረ**" ስር ተመ.

ከንዋታ ቅ ዘዋሪ፥ ስራ ፈት።

ከንፈር (ብ.ቁ **ከናፍር**) ስ 1.ከአፍንጫ በታች፥ ከአገጭ በላይ የሚገኝ የላይና የታች ጥርሶች ሽፋን፡ የአፍ ግጣም(ስእሉን ራስ ስር ተመ.)። በተጨማሪ "ለንቦጭን"ና "ምንጭር"ን ተመ. 2.ዳርቻ፥ ዳር፥ ጠርዝ። *ወንዙ ከንፈሩ ድረስ ሞልቷል።*

ከንፈሩን መጠጠ አዘነ።

ከንፈሩን ነከሰ ዛተ፥ አስፈራራ።

የከንፈር ቀለም ስ ከንፈርን ለማስዋብ የተዘጋጀ ማጌጫ ቀለም።

የከንፈር ወዳጅ ስ ፍቅረኛ (ከጋብቻ በፊት በወጣትነት ጊዜ የሚያዝና ግንኙነቱ በመሳሳም ላይ የተወሰነ)።

ከንፈራም ቅ ከንፈሩ ትልቅ የሆነ።

ከካ ግ 1.ጥሬ ጥሬን በወፍጮ በትልቅ በትልቁ ፈነከተ፡ ገረደፈ። 2.(ዘይ.) በብዛት ጠጣ፡ በላ፡ አወራ፡ (አልኮልን፥ ቆሎን፡ ወሬን፥...)። 3.ፈነከተ (በዱላ፡ በድንጋይ ጭንቅላትን)።

ክክ ስ ሳይደቅ በትልቅ በትልቁ በወፍጮ የተፈነከተ ወይም የተገረደፈ የጥሬ ጥሬ እህል።

ከዚህ "**እዚህ**" ስር ተመ.

ከዚያ "**እዚያ**" ስር ተመ.

*ከወረረ

ከውራራ (**ከወረር**) ግ ዘዋሪ፥ ቀውላላ።

ተንከዋረረ ግ ዞረ፥ ተንቀዋረረ።

አንከዋረረ ግ አዞረ፥ አንቀዋለለ።

*ከወተተ

ከወተት(ከውታታ) ቅ አውታታ፡ ከርታታ።

ተንከዋተተ ግ ተንከራተተ፡ ባዘነ።

ተንከዋታች ቅ ተንከራታች፡ ባዛኝ።

አንከዋተተ ግ አንከራተተ፡ አባዘነ።

ከወነ ግ 1.አዘጋጀ፡ አሰናዳ። 2.አስጌጠ፡ አሳመረ። 3.ፈፀመ፡ ጨረሰ።

***ከወከወ**

ከውካዋ (ከወከው፥ ከውከውቱ) ቅ ቀኸቃኻ፡ ቀውቃዋ፡ ዘዋሪ።

ከውከው አለ ግ ተንከወከወ።

ክውክው አደረገ ግ አንከወከወ።

ተንከወከወ ግ ተንቀገረቀገረ፡ ተንቀወቀወ፡ ዞረ።

አንከወከወ ግ አንቀገረቀገረ፡ አንቀወቀወ።

ከውር "**ኩየት**"ን ተመ.

ከውታታ "***ከወተተ**" ስር "**ከወተት**"ን ተመ.

ከውከውቱ "***ከወከወ**" ስር "**ከውካዋ**"ን ተመ.

ከውካዋ "***ከወከወ**" ስር ተመ.

ከዘራ

ከዘራ ስ በአንድ ጫፉ ቆልመም ያለ የእጅ መጨበጫ ያለው የእንጨት ወይም የብረት፥... ምርኩዝ።

ከይሲ ስ 1.የእባብ ሌላ ስም። 2.(ዘይ.፥ ስድብ) ክፉ፡ ተንኮለኛ፡ እርጉም።

ከደነ ግ 1.ገጠመ፥ ዘጋ (ክፍት የሆነ እቃን)። 2. ሸፈነ፡ አለበሰ (የቤት ጣሪያን በሳር፥ በቆርቆሮ፥...)።

መክደኛ ስ የተለያዩ ነገሮችን ለሚይዙ ወይም ለሚከቱ እንደ በርሜል፥ መሶብ፥ ድስት፥... ላሉ የእቃዎች አፍ የሚሆን መዝጊያ፥ መግጠሚያ።

ክዳን ስ 1.ግጣም፡ መክደኛ፥ እፊያ። 2.ለቤት ጣሪያ መክደኛ ወይም መሸፈኛ የሚሆን ሳር ወይም ቆርቆሮ።

ከዳ ስ ማሩ ተመጦ ባዶውን የቀረ ሰፈፍ፡ ገጋ።

ከዳ ግ 1.ኮበለለ፡ ሸሸ፡ ጠፋ (ለምሳሌ ከሃገር)። 2.በእምነት፥ በእምቢተኝነት ትቶ ሄደ (ከሰራዊት፥ ከፖለቲካ ድርጅት፥...)። 3.ግንኙነቱን ላቋረጠ፥ ተወ። *ገንዘብ ሲያጣ ጓደኛው ከዳው*። 4.አልታዘዝ አለ። *እግሩ ከዳው*። 5.ሸሸ፡ ጣለ፥ አንሸራተተ። *የቆመበት መሬት ስለከዳው ወደቀ*። 6.አሌ አለ፡ ሸፈጠ፥ ካደ። 7.አዘናግቶ ነከሰ (ውሻ)።

ከዳተኛ ቅ የገባውን ቃል፡ የተማለበትን አደራ ወይም እምነት የሚያፈርስ፡ የሚያጎድል።

ከጀለ ግ ተመኘ፥ ጓጓ፡ ፈለገ፡ ቋመጠ።

ክጀላ ስ ምኞት፡ ጉጉት።

ከፈለ ግ 1.ሁለት አደረገ፡ ሰነጠቀ፡ ገመሰ። 2.ለየ፡ ነጠለ፡ ለየብቻ አደረገ። 3.ቀነሰ፡ አጎደለ (ከአንድ ነገር ላይ)። 4.ለገዛው ነገር ዋጋውን ለሻጩ ሰጠ። 5. መልስ ሰጠ፡ መለሰ (ብድርን፡ ውለታን፡...)። 6.ሽንቱን ሸና።

መክፈያ ስ እንደ ጋጋ፡ ቅል፡... ያለ የሽንት መሽኛ እቃ።

ክፈል ቅ ገሚስ።

በክፈል ሙሉ በሙሉ ሳይሆን በግሚስ ወይም በተወሰነ መጠን።

ከፋይ "**ገንዘብ**" ስር "**ገንዘብ ከፋይ**"ን ተመ.

ክፋይ ቅ ቁራጭ፡ ቁራሽ።

ክፍል ቅ 1.ወገን። 2.ፋንታ፡ ድርሻ፡ እጣ። ስ 3.ምድብ። 4.በግድግዳዎች የተከፋፈለ የአንድ ቤት ውስጣዊ አካል። 5.በትምህርት ቤት ለመማሪያ የሚያገለግል ቤት። 6.የተወሰነ ትምህርት በተወሰነ ደረጃና ይዘት ተመጥኖ የሚሰጥበት የትምህርት ምድብ። *1ኛ ክፍል / 2ኛ ክፍል*። 7.በአንድ መስሪያ ቤት የተወሰነ ስራን የሚያካሂድ አካል። *ሂሳብ ክፍል*። 8.በአንድ ምእራፍ ውስጥ የሚገኝ ንኡስ ምእራፍ።

ክፍለ ሃገር ስ በውስጡ ብዙ አውራጃዎችን የሚያቅፍ የአንድ ሃገር የተወሰነ አቢይ የአስተዳደር ክልል።

ክፍለ አለም ስ ከሰባቱ ታላላቅ የአለም ክፍሎች (አፍሪካ፡ እስያ፡ አውሮፓ፡...) አንዱ፥ አህጉር።

ክፍለ ዘመን ስ የአንድ መቶ አመት ጊዜ።

ክፍለ ጊዜ ስ አንድ ነገር በቋሚነትና በተደጋጋሚ የሚፈፀምበት የተወሰነ የጊዜ ርዝመት።

ክፍለ ጦር ስ በወታደራዊ የሰራዊት ክፍፍልና ምደባ በስሩ ብዙ ብርጌዶችን አካቶ የያዘ የእግረኛ ሰራዊት ስብስብ ወይም ምድብ።

የክፍል ስራ ስ ተማሪዎች በትምህርት ሰአት ክፍል ውስጥ እንዲሰሩት ወይም እንዲመልሱት የሚሰጣቸው ጥያቄ፥ መልመጃ።

ክፍያ ስ ለአንድ ለተደረገ፥ ለተገዛ፥... ነገር ወይም ለተሰጠ አገልገሎት የሚከፈል ዋጋ፥ ገንዘብ።

ከፋፈለ ግ አንድ ላይ እንዳይሆን አደረገ፥ ለያየ።

ከፋፍለህ ግዛ በህዝቦች መካከል የዘር፡ የሃይማኖት፥... ልዩነትን ወይም አለመግባባትን በመፍጠር የሚካሄድ የአገዛዝ ስልት።

ክፍልፋይ ስ እንደ ½፡ 2/4፡ ¾፡ ⅔፡... ያሉ ቁጥሮች ወይም የምጣኔ መግለጫዎች።

ተካፈለ ግ 1.አብሮ ሆነ፡ ተገኘ፡ ተሳተፈ (በሃዘን፡ በደስታ፡ በስብሰባ፥...ላይ)። 2.ተጋራ፡ ድርሻውን ወሰደ። 3. ተከፋፈለ።

ተካፋይ ቅ 1.አብሮ የሚሆን፡ የሚገኝ፡ የሚሳተፍ (በደስታ፡ በሃዘን፡... ጊዜ)። 2.ንብረትን የሚካፈል፡ የሚጋራ፡ ባለድርሻ።

ተካፋይ ቁጥር ስ አንድ ቁጥር በሌላ ቁጥር ሲካፈል የሚከፈለው ቁጥር። ለምሳሌ አራት ለሁለት ቢካፈል (4÷2) 4 ተካፋይ ቁጥር ነው።

ተከፋፈለ ግ 1.ተለያየ፡ ተነጣጠለ፡ ለየብቻ ሆነ። 2.ድርሻ ድርሻውን ወሰደ፡ ተቀራመተ።

አካፈለ ግ 1.አጋራ፡ ድርሻ ድርሻውን ሰጠ። 2.ሁለት አደረገ፡ ገመሰ። 3.አዋየ፡ አማከረ (ለሃሳብ)።

ማካፈል ስ ከአራቱ የሂሳብ መደቦች አንዱ የሆነና አንድ የተወሰነ ቁጥር ለሌላ የተወሰነ ቁጥር እኩል እንዲዳረስ፡ እንዲሸነሸን የሚያደርግ የስሌት ዘዴ።

አካፋይ ቅ አጋማሽ።

አካፋይ ቁጥር ስ አንድ ቁጥር የሚካፈልበት ሌላ ቁጥር። ለምሳሌ አራት ለሁለት ቢካፈል (4÷2) 2 አካፋይ ቁጥር ነው።

አከፋፈለ ግ 1.ድርሻ ድርሻውን ሰጠ። 2.ወደ ተለያየ ቦታ ወይም አቅጣጫ እንዲዳረስ ወይም እንዲሰራጭ አደረገ።

ማከፋፈያ ስ 1.ማደያ። 2.ማሰራጫ።

አከፋፋይ ቅ ወደ ተለያየ ቦታ ወይም አቅጣጫ እንዲዳረስ ወይም እንዲሰራጭ የሚያደርግ (ለምሳሌ ሸቀጥን)።

***ከፈለ**

መከፈልት (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ስ የሞተን ሰው ነፍስ ለማስማር ሲሉ የሟች ዘመዶች በቤተክርስቲያን ለካህናት የሚያቀርቡት ምግብና መጠጥ፡ ፀበል ፀዲቅ፡ የቆራቢ እራት።

አከፈለ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ግ ከፀሎተ ሃሙስ ወይም ከስቅለት ማታ ጀምሮ እስከ ትንሳኤ ሌሊት ድረስ ምግብና መጠጥ ሳይቀምስ ቆየ ወይም ፆመ።

አክፋይ ስ የሚያከፍል፡ ከፀሎተ ሃሙስ ወይም ከስቅለት ማታ ጀምሮ እስከ ትንሳኤ ሌሊት ምንም ሳይቀምስ የሚፆም ሰው።

የአክፋይ ስ ለሚያከፍል ሰው የሚደረግ ስጦታ (አብዛኛውን ጊዜ ምግብና መጠጥ)።

አክፍሎት ስ ምግብና መጠጥ የማይቀመስበት ከፀሎተ ሃሙስ እስከ ትንሳኤ ድረስ ያለው የምና የፆም ጊዜ።

ከፈረረ ግ በጣም ደረቀ፥ ቀፈረረ።

ከፈረር (ክፍራራ) ቅ በጣም የደረቀ፥ ቀፍራራ።

ተንከፈረረ ግ 1.በጣም ደረቀ፥ ተንቀፈረረ። 2.(ዘይ.) ሞተ።

እንክፍር ቅ በጣም የደረቀ፥ እንቅፍር።

ከፈተ ግ 1.የተዘጋን የበር፥ የመስኮት፥... መዝጊያ ወይም መክለያ ዘወር ወይም ገለል በማድረግ ዝግ የነበረው በር፥ መስኮት፥... ክፍት እንዲሆንና መግባትና መውጣት እንዲቻል አደረገ። 2.ግጣምን ወይም መክደኛን አነሳ፥ አስወገደ። (ለምሳሌ የመሶብን፥ የድስትን፥... ግጣም)።3.መተላለፊያ መንገድ ሰጠ ወይም ለቀቀ። 4.አላቀቀ፥ ፈታ (የበር፥ የሳጥን ቁልፍን)። 5.ጀመረ። *ስብሰባውን በንግግር ከፈተ*። 6.አቋቋመ፡ ሰራ። *ት/ቤት ከፈተ*። 7.ክፍት፡ ብሩህ አደረገ (አእምሮን፥ ልብን)። 8.ገለጠ፥ በራ፥ ወለል አለ፥ ለቀቀ (ጭጋግ፥ ጉም፥...)።

ቢከፍቱት ተልባ 1.ከላይ ወይም ከውጪ ሲታይ ደህና የሚመስል፥ ግን ውስጡ መናኛና የማይረባ ሆኖ የሚገኝ። 2.ቁም ነገር የሌለው።

መክፈቻ ስ 1.የተቆለፈን መፍቻ ወይም ቁልፍ። 2.እንደ ቆርቆሮ፥ ጠርሙስ፥... ያሉትን እቃዎች ከዳን ወይም ግጣም ለመክፈት የተሰራ መሳሪያ።

የመክፈቻ ንግግር ስ በስብሰባ፥ በሴሚናር፥... ላይ የሚደረግ የመግቢያ ወይም የመጀመሪያ ንግግር።

ክፍታ ቅ 1.ለጥሩ ሁኔታ የማይከደን ወይም ያልተከደነ። 2.አፈ ሰፊ እቃ።

ክፍት ቅ 1.ያልተዘጋ፥ ያልተከደነ። 2.ተከፋች የሆነ። 3.ያልተያዘ። *ክፍት ቦታ*።

ክፍት መኪና ስ ከበስተኋላው ከፈን የሌለው መኪና።

ክፍት ቦታ ስ ያልተያዘ ስፍራ።

ክፍት [አፍ] ቅ (ስድብ) 1.ጯሂ፥ ተሳዳቢ። 2.ባለጌ፥ ንግግሩ ያልታረመ፥ ጋጠወጥ። 3.ፈዛዛ፥ ነሆላላ።

ክፍት የስራ ቦታ ስ ሰራተኛ ያልተቀጠረበት የስራ መደብ።

ክፍተት ስ 1.ቀዳዳነት፥ ስንጥቃት። 2.የአንድ ነገር ግንኙነት መቋረጥና ክፍት ሆኖ መገኘት።

ተከፋች ቅ ተካፋች።

ተካፋች ቅ 1.የሚከፈት። 2.ዚፕ ወይም ቁልፍ ያለው (ልብስ)።

ከፈት ስ የሚመዘን እቃ የሚቀመጥበት የሚዛን ቆዳ(በእሉን ሚዛን ስር.)።

ከፈቸረ ግ በጣም ደረቀ፤ ከቸረ።

ክፍቻራ ቅ ክፍራራ፤ ደረቅ።

ከፈነ ግ በከፈን ሸፈነ፤ ጠቀለለ፤ ገነዘ (ሬሳን)።

ከፈን ስ የሬሳ መጠቅለያ ልብስ፤ መግነዝ።

ከፈከፈ ግ 1.የቤትን ግሪያ በክፍክፋት የአሰራር አይነት በሳር ከደነ። 2.አበጠረ፤ ከመከመ (ጎፈሬን)።

መክፍከፊያ ስ 1.ባለክፍክፋት የሳር ክዳን ቤት ሲሰራ የሳሩ ቂጥ እንዲስተካከል የሚተመተምበት ጠፍጣፋ እንጨት። 2.የፀጉር ማበጠሪያ።

ከፈክፍ ስ ክፍክፋት።

ክፍክፋት ስ ወጣ ገባ እንዳይኖረው ተደርጎ በመክፍከፊያ እየተተመተመ በጥንቃቄ የሚሰራ የሳር ቤት አከዳደን።

ክፍክፍ ስ 1.በክፍክፋት የአሰራር አይነት የተሰራ የሳር ቤት ክዳን። ቅ 2.በደንብ ተስተካክሎ የተበጠረ (ጎፈሬ)።

ከፈይ (ከፋይ) ስ ልጥፍ ያለ ለስላሳ ፀጉር ያለውና ወፈር ያለ የልብስ አይነት።

ከፈፈ ግ 1.ክፈፍ አበጀ። 2.ከረከመ፤ አስተካከለ (የአንድን ነገር ጠርዝ፤ ግርጌ)።

ክፈፍ ስ ለውበት ወይም ለጥንካሬ ተብሎ በአንድ ነገር ጫፍ ዙሪያ ላይ የሚሰፋ ወይም የሚለበድ እንደ ጨርቅ፤ እንጨት፤ ቆርቆሮ፤... ያለ ጠርዝ።

ከፈል "**ከፈለ**" ስር ተመ.

ከፋ ግ 1.መጥፎ ሆነ፤ ጨከነ፤ ክፉ ሆነ። 2.ባሰ፤ ጠና፤ በረታ፤ የበለጠ ተበላሸ (ለመጥፎ ነገር)።

ቢከፋም ቢለማም ቢሆንም ባይሆንም።

አይከፋም ምንም አይል፤ ይሁን፤ ደህና ነው።

ከፋው አዘነ፤ ተበሳጨ፤ ተከዘ።

ክፉ ቅ 1.መጥፎ፤ ጨካኝ። 2.ሰሰታም፤ ንፉግ። 3.ሃይለኛ።

ለክፉ አይሰጥም በጣም መጥፎ አይደለም፤ ደህና ነው።

በክፉ አይን አየ በጥላቻ አይን አየ።

ክፉና ደግ ተነጋገሩ የሚያቀያይም ወይም የሚያጣላ ነገር ተነጋገሩ።

ክፉ መንፈስ ስ ሰይጣን፤ ጋኔን።

ክፉ ቀን ስ በረሃብ፤ በበሽታ፤ በጦርነት፤... ምክንያት የሰውና የከብት እልቂት የደረሰበት ወይም የሚደርስበት ጊዜ።

ክፉኛ ተው.ግ. በጣም፤ በሃይል፤ በጽኑ። *ክፉኛ ታሟል*።

ክፋት ስ 1.መጥፎነት፤ ተንኮል። 2.ምቀኝነት።

ተከፋ ግ 1.አዘነ፤ ተከዘ። 2.ተበሳጨ፤ ተናደደ። 2. ተቀየመ፤ አኮረፈ።

አከፋ ግ 1.ክፉ እንዲሆን ምክንያት ሆነ። 2.አከፋፋ።

አከፋፋ ግ አጥላላ፤ አንቋሸሸ።

አክፋፋ ዝ.ከ.

አስከፋ ግ 1.አስቀየመ፤ አሳዘነ። 2.አስጠላ።

አስከፊ ቅ 1.መጥፎ፤ አስቀያሚ። 2.አሳዛኝ። *አስከፊ የሆነ እልቂት ደረሰ፤*

ከፋታ "**ከፈተ**" ስር ተመ.

ከፋይ "**ከፈይ**"ን ተመ.

ከፍ

ከፍታ ስ 1.ከአካባቢው መሬት ወደ ላይ ላቅ ያለ መሬት፤ ጉብታ። 2.አንድ ነገር ከመሬት ወደ ላይ ሲለካ የሚኖረው ርዝመት። 3.ብልጫ።

ከፍተኛ ቅ 1.ከፍታ ያለው። 2.ትልቅ። 3.የበላይ። 4.በከተማ ውስጥ የተወሰኑ ቀበሌዎችን አጠቃሎ እንዲይዝ የተደረገ የተወሰነ የቦታ ክልል ወይም አስተዳደር።

ከፍ አለ ግ 1.ወደላይ ወጣ አለ። 2.በለጠ፤ ላቀ። 3.አደገ፤ በዛ፤ ጨመረ (መጠኑ፤ ቁጥሩ፤...)።

ከፍ አደረገ ግ 1.ወደ ላይ ብድግ አደረገ። 2.አበለጠ፤ አላቀ፤ ክብር ሰጠ። 3.አበዛ፤ ጨመረ (በመጠን፤ በቁጥር፤...)።

ከፍ ከፍ አለ ግ በለጠ፤ ላቀ፤ ክብር አገኘ።

ከፍ ከፍ አደረገ ግ አላቀ፤ ክብር ሰጠ።

ከፍ ዝቅ አደረገ አዋረደ (በስድብ፤ በማልምጫ፤...)።

ክፍራራ "**ከፈረረ**" ስር "**ከፈረር**"ን ተመ.

ከፍተኛ "**ከፍ**" ስር ተመ.

ከፍታ ዝ.ከ.

ክፍቻራ "**ከፈቸረ**" ስር ተመ.

ኩ ተ "**ከ**" ፊደል ካዕብ ዘር።

—ኩ —ሁ ን ተመ.

ኩሊ ስ 1.በሸክም ስራ የሚተዳደር ሰው፤ ሸቃይ። 2.የቀን ሰራተኛ።

ኩሊሊት ስ በመጠን ከርግብ አነስ የሚል፤ መልኩ አሸዋማ ሆኖ ረጃጅምና ቀጭን የሆነ ቀይ ቅልጥም ያለው፤ ማታ ወይም ሌሊት ላይ በሰው ወይም አውሬ ሲያዝ የሚጮህ ወፍ፤ ሊብ ጠረም ይባላል።

ኩላሊት ስ በሰው ወይም በእንስሳ ሰውነት ውስጥ በወገብ አካባቢ ከጀርባ በኩል ጥንድ ሆኖ የሚገኝ ከደም ውስጥ ቆሻሻ ፈሳሽን ወይም ሽንትን የሚያጣራ የሰውነት ክፍል።

ኩላሊት

ኩላብ ስ ሚዷንጠ::

ኩል "ኳለ" ስር ተመ.

ኩልል ኩልል አለ ግ ወንድ አህያን ጠራ (የወሲብ ፍላጎቱ እንዲነሳሳ)::

ኩልሽ "*ኮለሸ" ስር ተመ.

ኩልትፍ "*ኮለተፈ" ስር"ኩልታፋ" ን ተመ.

ኩልኩል ዶሮን ለመጥራት የሚባል ቃል::

ኩልኩልት ስ 1. በበግና በፍየል አንገት ላይ በበሽታ ምክንያት የሚወጣ እንደ እንቅርት ያለ እብጠት:: 2.ከድሎት የተነሳ ከአገጭ ስር በሰው አንገት ላይ የሚንጠለጠል ውፍረት ወይም ስጋ::

ኩልኩልቲያም ቅ (ስድብ) ኩልኩልት ያለበት (ሰው)::

ኩልፍልፍ "ኮለፈ" ስር ተመ.

ኩም

ኩም አለ ግ አፈረ፣ ደነገጠ (ያልጠበቀው ስለሆነበት)::

ኩም አደረገ ግ አሳፈረ፣ አስደነገጠ::

ኩምሽሽ

ኩምሽሽ አለ 1.ጭብጥ፣ ኩርምት አለ:: 2. አፈረ፣ ተሸማቀቀ፣ ደነገጠ::

ኩምቢ (ኩንቢ) ስ የዝሆን አፍንጫ(የዝሆንን ስእል ተመ.)::

ኩምት ስ የክርን ላይ እከክ::

ኩምችች

ኩምችች አለ ግ 1.አጥር፥ አነስ አለ:: 2.ኩርችች አለ:: 3.አፈረ፣ ተሸማቀቀ::

ኩምችች አደረገ ግ 1.አሳጠረ፥ አሳነሰ:: 2.አሳፈረ፣ አሸማቀቀ::

ኩምክና "ኮመከ" ስር ተመ.

ኩረጃ "ኮረጀ" ስር ተመ.

ኩሩ "ኮራ" ስር ተመ.

ኩሩምባ "ኩርምባ"ን ተመ.

ኩሩሩ ቅ በጣም አጭር::

ኩራተኛ "ኮራ" ስር ተመ.

ኩራት ዝ.ከ.

ኩሬዝ ስ 1. መጠኑ ከቀለም ብልቃጥ ትንሽ ከፍ የሚል፥ ለክርና ለሳምባ ወይም ለናፍጣ ማስገቢያ የሚሆን ጠባብ አፍ ያለውና በውስጡ የሚገኘው ክር ጫፉ ሲቀጣጠል ብርሃን የሚሰጥ የመብራት እቃ:: 2.(ዘይ.) አጭር (ሰው)::

ኩሬ ስ በጥልቀትም ሆነ በስፋት መጠኑ ከሃይቅ አነስተኛ የሆነ፣ የተጠራቀመና የማይንቀሳቀስ ውሃ::

ኩርማ ስ ክርን::

ኩርማን ቅ የአንድ ነገር አንድ አራተኛው ክፍል (የእንጀራ፣ የመሬት፣...)::

ኩርምባ (ኩርንባ) ስ ጥቅል ጎመን::

ኩርምባጥ (ቁርምባጥ) ቅ አጭርና ቀጭን (ሰው)::

ኩርር... 1.ተደጋግሞ ሲነገረው ያልሰማን ሰው ጆሮህ አይሰማም? ለማለት ተናጋሪው በቁጣ የሚያሰማው ድምፅ:: 2.አንድ የሚረብሽ ነገር ወይም ድምፅ ጆሮ ውስጥ ሲኖር፣ የሚረብሸውን ነገር ለማስወገድ ጆሮ ውስጥ በመፈጥህ የሚያሰሙት ድምፅ::

ኩርሲ ስ ቢርጩማ::

ኩርሽሜ ስ ሲያኝኩት ከሽ ከሽ የሚል ድምፅ የሚኖረውና ለጥርስ የሚገራ እንደ ቃሪያ፥ ፍርምባ፣ እኒሳ፥.. ያለ ምግብ::

ኩርባ ስ መታጠፊያ፣ ማዞሪያ (የመንገድ)::

ኩርችች

ኩርችች አለ ግ ኩርምት ብሎ ተቀመጠ::

ኩርንችት ስ 1.መሬት ላይ ልጥፍ ብሎ የሚበቅል ጠንካራ እሾህ ያለው የእፅዋት አይነት:: 2.[illegible] ማያያዣ የሚያገለግልና መጠኑ በጣም ትንሽ የሆነ ምስማር::

ኩርኩር^1 አህያን ለመጥራት የሚያገለግል ቃል::

ኩርኩር^2 ስ 1.ባለ ሰስት ጎማ የሆነና እንደ ሞተር ቢስክሌት ያለ፥ከኋላው ሰው ሊጭን የሚችል መጓጓዣ:: 2በእጅ የሚገፋና እቃ ለማጓጓዣ የሚያገለግል ባለ አንድ ጎማ ጋሪ::



ኩርኩር 2ኛ ፍቺ

ኩርኩር አለ ግ ድክ ድክ፥ ውንክር ውንክር አለ::

ኩርኩም "ኮረከመ" ስር ተመ.

ኩርኳሚ ዝ.ከ.::

ኩርዲዳ ስ አራዊትን የሚያስለጥን ወይም

የሚገራ ሰው።

ኩርዷ ቅ ከርዳዳ (ለፀጉር)።

ኩርፊኛ "*ኮረፈ¹" ስር ተመ.

ኩርፍያ¹ ዝ.ክ.

ኩርፍያ² "ኮረፈ²" ስር ተመ.

ኩርፉድ ቅ አጭርና መልከ ጥፉ (ሰው)።

ኩርፉፍቻ (ኩርፉፊያ) ስ አፋኝት።

ኩርፍ "*ኮረፈ¹" ስር ተመ.

ኩርፍተኛ ዝ.ክ.

ኩርፍታም ዝ.ክ.

ኩሳ ስ ኩሽ።

ኩሳይ ቅ የኩሳ ዘር ወይም ወገን።

ኩሳንኩስ ስ ግሳንግስ፤ ኮተት፤ ቅራቅምቦ።

ኩሳይ "ኩሳ" ስር ተመ.

ኩስ "ኮሳ" ስር ተመ.

ኩስቱባን ስ የጣት ቤት፤ ልብስ ዘምባሚያዎች መርፌ እንዳይወጋቸው በጣታቸው ላይ የሚደፉት ከብረት የተሰራ የጣት ቆብ።

ኩስታሪ "ኮስተረ¹" ስር ተመ.

ኩስ ኩስ

ኩስኩስ አለ ግ ቱስ ቱስ አለ (የአካሄድ አይነት)።

ኩስኩስት ስ 1.ከሸክላ ወይም ከነሃስ፤... በጀበና ቅርፅ የሚሰራ የእጅ ማስታጠቢያ። 2.የቡና ጀበና (ጎጃም)።

ኩስኩስት 1ኛ ፍቺ

ኩሽተኛ "ኳሸ" ስር ተመ.

ኩሽት ዝ.ክ.

ኩሽና ስ ማድቤት፤ ወጥ ቤት።

ኩሽኔታ (ኩችኔታ) ስ በአንድ ማሽን ውስጥ እንቅስቃሴ እንዲኖር የሚረዳና ፍትጊያን የሚቀንስ ክብ ሆኖ በውስጡ ድቡልቡል የብረት ብዮች ያሉበት መሳሪያ።

ኩበት ስ የደረቀ የከብት እበት።

ኩበት ወረራ ስ የዳግማይ ትንሳኤ ማግስት ሰኞ፤ ከበአሉ በኋላ ስራ የሚጀመርበት የእጅ ሟሟሽ ቀን።

ኩባንያ ስ ህጋዊ ሰውነት ያለው ግለሰቦች በህብረት የሚያቋቁሙት የንግድ ድርጅት።

ኩባያ ስ ከኒኬል ወይም ከፕላስቲክ ወይም ከሸክላ፤... የሚሰራና እንደ ብርጭቆ ወይም ዋንጫ ለመጠጫ የሚያገለግል እቃ።

ኩብ "*ኮበከበ" ስር ተመ.

ኩብኩባ ዝ.ክ.

ኩተት ስ 1.የተናንሽ የልጅ ወይም የፈረስ ቀንድም። 2.የህፃንነት ጊዜ ወይም ዘመን። *ከኩታት እስከ ሽበት እንዲሉ*።

ኩቲ ስ 1.ውሻን ለመጥራት የሚያገለግል ቃል። 2.ውሻ።

ኩቲሳ (ቁጢሳ) ስ የውሻ ግልገል፤ ቡችላ።

ኩታ ስ ድርና ማግ ቀጭን ሆኖ በሁለት ነጠላ መጠን ከተሰራ በኋላ እጥፉን ተሰፍቶ እንደ ጋቢ የሚለበስ ሸማ።

ኩታ ገጠም ስ ድንበርተኛ፤ ወሰንተኛ።

ኩታራ ስ 1.ጉብል፤ ብላቴና። 2.ተራ፤ አልባሌ ሰው።

ኩት ዶሮን ሂድ ወይም ወግድ ለማለት የሚባል ቃል።

ኩት [ውሃ] ስ በየካቲት ወር የሚወጣ የኮከብ አይነት። በተጨማሪ "**ኮከብ ቆጠራ**"ን ተመ.

ኩትኮታ "ኮተኮተ" ስር ተመ.

ኩትኳቶ ዝ.ክ.

ኩነኔ "ኮነነ" ስር ተመ.

ኩንስንስ "*ኮነሰነሰ" ስር ተመ.

ኩንቢ "ኩምቢ"ን ተመ.

ኩንታል ስ አንድ መቶ ኪሎ የሚመዝን ማንኛውም እቃ።

ኩንትሽ "ኮነተሸ" ስር ተመ.

ኩኩሉ (አኩኩሉ) 1.የወንድ ዶሮ ጩሀት። 2.የልጆች የድብብቆሽ ጨዋታ ስም።

ኩኩ መለኮቴ ስ 1.ዋኔ የምትጠራበት ሌላ ስም። 2.የዋኔ ጩሀት። 3.ልጆች እያዜሙ የሚጫወቱት የጨዋታ አይነት።

ኩኪ ስ የጆሮ ግንድ።

ኩክ ስ ጆሮ ውስጥ የሚገኝና መጣበቅነት ያለው ቅባት።

ኩክ ማውጫ ስ ከጆሮ ውስጥ ኩክ ለማውጣት የሚያገለግል የማንኪያ ቅርፅ ያለውና መጠኑ ትንሽ የሆነ መሳሪያ።

ኩክኒ ስ 1.ጭርት። 2.ነጭ እከክ።

ኩክኒያም ቅ (ለድብ) ኩክኒ ያለበት።

ኩየት (ከውር) ስ ብር ወይም ወርቅ ከቀለጠ በኋላ የተፈለገውን ቅርፅ ይዞ እንዲወጣ ለማድረግ የሚያገለግል የእንጥረኛ መሳሪያ።

ኩይሳ "ኮየሰ" ስር ተመ.

ኩዳዴ "ሁዳዴ"ን ተመ.

ኩዳድ "ሆደደ^{1}" ስር "ሁዳድ"ን ተመ.

ኩዴታ ስ መፈንቅለ መንግስት።

ኩፌት ስ ቆብ፥ ባርኔጣ።

ኩፍስ "ኮፈሰ" ስር ተመ.

ኩፍታ "*ኮፈፈ" ስር ተመ.

ኩፍታ ዘ.ከ.

ኩፍታ ስ ሙስሊሞች፥አይሁዶችና ካቶሊኮች የሚያደርጉት ክብና ትንሽ የሆነ ቆብ።

ኩፍኝ ስ ኃይለኛ ትኩሳት የሚያስከትልና እንደ እከክ በሰውነት ላይ የሚወጣ የህፃናት በሽታ።

ኩፍ ጫማ ስ ባለ ተረከዝ ሽፍን ጫማ።

ኪ የ "ከ" ፊደል ሳልስ ዘር።

ኪሎ ሜትር ስ አንድ ሺህ ሜትር የሆነ የርዝመት መለኪያ።

ኪሎ ዋት ስ የኤሌክትሪክ ሃይል (ጉልበት) መለኪያ።

ኪሎ ግራም ስ አንድ ሺህ ግራም የሚመዝን የክብደት መለኪያ።

ኪራይ "*ከረየ" ስር ተመ.

ኪሮሽ (ኪርሼ) ስ ዳንቴል ለመስራት የሚያገለግልና ጫፉ ቆልማማ ብሎ የተሰራ ቀጭን ሽቦ።

ኪሳራ "ከሰረ" ስር ተመ.

ኪስ ስ 1.እንደ ሱሪ፥ ቀሚስ፥ ኮት፥... ባሉ ልብሶች ላይ ተሰፍቶ የሚገኝና አነስተኛ እቃዎችን ለመያዝ የሚያገለግል እንደ ከረጢት ያለ የልብሱ ክፍል። 2.የጠረጴዛ፥ የቁም ሳጥን፥... መሳቢያ።

ኪሱ ተራቆተ ኪሱ ባዶ ሆነ፥ ገንዘብ አጣ።

ኪስ በርባሪ ቅ ኪስ አውላቂ፥ ሌባ።

ኪስ ቦታ ስ በቤቶች መካከል የሚገኝ፥ ቤት ያልተሰራበትና ባለቤት የሌለው ባዶ ቦታ።

ኪስ አውላቂ ስ ከሰዎች ኪስ ገንዘብ የሚሰርቅ ሌባ።

የኪስ መዝገበ ቃላት ስ በኪስ ለመያዝ በሚያመች ቅርፅ የተዘጋጀ፥ መሰረታዊ ቃላትንና ፍቺዎቻቸውን በአጭሩ የያዘ መዝገበ ቃላት።

የኪስ ሰአት ስ በኪስ የሚያዝ ባለሰንሰለት ሰአት።

የኪስ ገንዘብ ስ ለጥቃቅን ጉዳዮች ይውል ዘንድ አንዳንድ ትምህርት ቤቶች ለተማሪዎቻቸው እንዲሁም ወላጆች ለልጆቻቸው የሚሰጡት አነስተኛ ገንዘብ።

ኪታ ስ ትንሽ ጥብቆ።

ኪነ

ኪነ (ኪነት) ቃል ስ ስነቃል።

ኪነ ጥበብ ስ እንደ ሳእል፥ ቅርፃ ቅርፅ፥... ያለ የእጅ ጥበብ ስራ።

ኪነት ስ 1.ኪነ ጥበብ። 2.የሙዚቃ፥ የዘፈን፥ የውዝዋዜ ጥበብ።

ኪኒን ስ በፍሬ ወይም በእንክብል መልክ የሚዘጋጅ የህመም ማስታገሻ መድሃኒት።

ኪንታሮት ስ 1.መጠኑና ቅርፁ እንደብጉር ሆኖ አብዛኛውን ጊዜ በእጅና በእግር ላይ እየወጣ ረዘም ላለ ጊዜ የሚቆይ ጠንካራ፥ ሸካራና እንደ አትራት ያለ የቆዳ በሽታ። 2.የእህያ ኪንታሮት።

ካ የ "ከ" ፊደል ራብእ ዘር።

ካህን "ካነ" ስር ተመ.

ካሊም ስ ከወፍራም ክር የተሰራ፥ ዥንጉርጉር የሆነና እንደ ኣልጋ ልብስ ወይም ምንጣፍ የሚያገለግል ልብስ።

ካልሲ ስ ከሱፍ ወይም ከናይለን፥... በእግር ጫማ ልክ የሚሰራ፥ የእግር ማስገቢያ ያለው፥ እስከ ጉልበት ሊደርስ የሚችል የእግር ልብስ ወይም መሸፈኛ፥ የእግር ሹራብ ።

ካልሲየም ስ ነጭና ለስላሳ ሆኖ ለህይወት የሚያስፈልጉ የብዙ ነገሮች ውህድ የሆነ፥ በጥርስና በአጥንት ውስጥ የሚገኝ ንጥረ ነገር።

ካልቾ ስ በእግር ጫፍ በላይኛው ክፍል የሚደረግ ምት።

ካሉስ ስ የሃር ክር አይነት።

ካሚዮን ስ የጭነት መኪና።

ካሜራ ስ የፎቶግራፍ ማንሻ መሳሪያ።

ካምቦሎጆ "ስታዲየም"ን ተመ.

ካምፕ ስ 1.ወታደራዊ የጦር ሰፈር። 2.ሰፈር።

ካሪ "ካሬ"ን ተመ.

ካራ ስ ቢላዋ።

ካራቴ ስ በሩቅ ምስራቃውያን ዘንድ የተለመደና መሳሪያ ባልያዙ ሰዎች መካከል በእጅ፥ በእግር፥ በራስ የሚከናወን ሃይለኛና ጥበባዊ የአመታት ዘዴ።

ካራት ስ 1.አንድ ወርቅ የወርቅነቱ ደረጃ ወይም ጥራቱ ምን ያህል እንደሆነ የሚገለፅበት መለኪያ። 2.የከበሩ ድንጋዮች ክብደት መለኪያ።

ካሬ (ካሪ) ስ ፥ መረባ አራት እኩል ጎኖችና ማእዘኖች ያሉት ቅርፅ።

ካሬ ሜትር ስ በአራቱም ጎኖቹ በኩል አንድ አንድ ሜትር ርዝመት ያለው ቅርፅ ወይም ወለል፡ መረብ ሜትር።

ካሬ ኪሎ ሜትር ስ በአራቱም ጎኖቹ በኩል አንዳንድ ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው ቅርፅ ወይም ወለል ፡ መረብ ኪሎ ሜትር።

ካሬታ የ "**ኩርኩር**^{2}"ን 2ኛ ፍቺ ተመ.

ካርቡሬተር ስ ቤንዚንን ከነፋስ አደባልቆ ለሞተሩ የሚያቀብል የመኪና አካል።

ካርባይን ስ የጠበንጃ አይነት (በጥንት ጊዜ የፈረሰኛ ወታደር ትጥቅ)።

ካርቦሃይድሬት ስ ካርቦን፡ ሃይድሮጅንና ኦክስጅን በውስጡ ያለበት እንደ ስኳር፡ ስታርች፡ ሴሉሎስ፡ ... ያለ ንጥረ ነገር።

ካርቦን ስ 1.እንደ አልማዝ፡ ግራፋይት፡የድንጋይ ከሰል፡... ባሉ ማእድናት ውስጥ በተጣራ መልኩ፡ እንዲሁም ህይወት ባላቸው ነገሮች ውስጥ በቅይጥነት የሚገኝና ብረትነት የሌለው ንጥረ ነገር። 2.በሳዩ ላይ የሚፃፍበት የማንኛውም ነገር ትክክለኛ ቅጂ ከስሩ በሚገኘው ሌላ ወረቀት ላይ እንዲቀረፅ የሚያደርግ፡ በካርቦን ወይም በሌላ ነገር ተቀልሞ የሚዘጋጅ ስስ ወረቀት።

ካርቦንሞኖክሳይድ ስ ከተቃጠለ ካርቦንና በነዳጅ ከሚንቀሳቀሱ ሞተሮችና ማሽኖች የሚወጣ መርዝነት ያለው ጭስ።

ካርቦንዳዮክሳይድ ስ ሰውና እንስሳ ወደ ውጪ ሲተነፍሱ ወይም አንዳንድ ነገር ሲቃጠል የሚወጣ የተቃጠለ አየር (ጋዝ)።

ካርቱን ስ ስለአንድ ሰው ወይም ሁኔታ በሰዎች አስተያየት ላይ ተፅእኖ ለማሳደር ወይም አንድ አይነት መልእክት ለማስተላለፍ በአስቂኝ (ከተፈጥሮ መልኩ ለየት ባለ) ሁኔታ የሚሰራ የስእል አይነት።

ካርቱን ፊልም ስ በተንቀሳቃሽ ፊልም የሚቀርብ የካርቱን ስእል።

ካርታ^{1} ስ 1.የአገሮችን፡ የውቅያኖሶችን፡ የወንዞችን፡ የተራሮችን፡... የቦታ ክልል ወይም አንድን የተወሰነ ቅርፅ የሚያሳይና በወረቀት፡ ... ላይ የተሰራ ስእል፤ የመሬት የተወሰነ ክፍል ወይም ቅርፅ። 2.ለጊዜ ማሳለፊያ፡ ለቁማር፡ ለጨዋታ የሚያገለግል ልዩ ልዩ ስእሎች ወይም ቁጥሮች ያሉበት ካርድ።



ካርታ 2ኛ ፍቺ

ካርታ^{2} ስ የጥይት ማቀፊያ ወይም መያዣ።

ካርቶን ስ 1.ወፍራም ወረቀት ወይም ክርታስ። 2.ከወፍራም ወረቀት ወይም ክርታስ እንደ ሳጥን ሆኖ የሚዘጋጅ የእቃ መያዣ።

ካርኒ ስ በተለያዩ ምክንያቶች እቃ ወይም ገንዘብ ገቢ ወይም ወጪ መሆኑን ወይም መሸጡን ለማረጋገጥ የሚዘጋጅ የፅሁፍ ማስረጃ።

ካርኒ ቆረጠ ካርኒ ሸጠ ወይም ገዛ።

ካርኒ ቆራጭ ስ ገንዘብ እየተቀበለ ካርኒ የሚሸጥ ሰው።

ካርድ ስ የተለያዩ ጉዳዮች የሚፃፉበት፡ ብዙውን ጊዜ መጠኑ አነስተኛ የሆነና ወፈር ያለ ወረቀት (ራሽን ካርድ፡ ሪፖርት ካርድ፡ የሃኪም ቤት ካርድ፡ ፖስታ ካርድ፡ የተማሪዎች ውጤት መግለጫ ካርድ፡...)።

ካሮት ስ ስሩ የሚበላ፡ ቀለሙ በቀይና በቢጫ መካከል የሆነ የተክል አይነት። የሚበላው ክፍልም ካሮት ይባላል።

ካሮት

ካስ ግ ካሳ ሰጠ፡ ከፈለ ወይም ሌላ ጠቀሜታ ያለው ነገር አደረገ (በዳይ ለተበዳይ)።

ካሳ ስ በዳይ ለተበዳይ የሚሰጠው ወይም የሚከፍለው ወይም የሚያደርገው ማንኛውም ነገር።

ካሳ ቆረጠ የካሳውን አይነትና መጠን ወሰነ።

ካሳ በላ ካሳ ተቀበለ።

ተካሰ ግ ካሳ ተቀበለ፡ ወሰደ፡ አገኘ።

ተካካሰ ግ 1. ተጣጣ፡ ተቻቻለ፡ የጎደለው በሌላ ተሟላ። 2. ለደረሰበት ችግር፡ በደል፡... ማካካሻ፡ መርጃ፡ መፅናኛ፡... የሚሆን ጥቅም አገኘ።

አካካሰ ግ አጣጣ፡ አቻቻለ።

ካሴት ስ የቴፕ ወይም የቪዲዮ ክር።

ካስማ ስ የድንኳንን አውታር ወጥሮ ለመያዝ የሚያገለግል ራሱ ቀላፋ እንጨት ወይም ብረት፡ ችካል(ስእሉን ድንኳን ስር ተመ.)።

ካስክ ስ በኤሌክትሪክ የሚሰራና የረጠበ የራስ ጠጉርን በሙቀትና በነፋስ ሃይል ለማድረቅ የሚያገለግል መሳሪያ።

ካሸር ስ የባንክ፥ የግምጃ ቤት፥ የሆቴል ቤት፥... ገንዘብ ተቀባይ ወይም ከፋይ።

ካሽ ስ ጥሬ ገንዘብ።

ካበ ግ 1.ድንጋይን በድንጋይ ላይ በማነባበር የድንጋይ አጥር ወይም የድንጋይ ግድግዳ ሰራ። 2.ቆለለ፥ ከመረ። 3. አሞገሰ፥ አሞካሸ፥ ከፍ ከፍ አደረገ።

ካብ ስ ድንጋይን በድንጋይ ላይ በማነባበር የሚሰራ አጥር ወይም ግድግዳ።

ካቡት ስ ባለመክፈቻ ረጅም ቀሚስ።

ካቢኔ ስ በአንድ መንግስት ርእሰብሄር ተመርጠው የመንግስትን ፖሊሲና አስተዳደር በሃላፊነት የሚመሩ የሚኒስትሮች ቡድን።

ካባ ስ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል ድንጋይ የሚገኝበትና የሚፈለጥበት ቦታ።

ካባ ስ ቅርፁ ክብ ሆኖ ከፊት በኩል ክፍትነት ያለው ከሱፍ ወይም ከሃር፥ ... የሚሰራና ከልብስ በላይ የሚለበስ መደረቢያ።

ካባ ላንቃ (ላንቃ ካባ) ቅ ያንገቱና የትከሻው ዙሪያ የለምድ ቅርፅ ባለው የወርቅ ጥልፍ የተጌጠ የካባ አይነት።

ካቢላ ቅ 1.የኮቴው ጥፍር አድጎ ወደላይ የተቆለመመ (አህያ)። 2.(ስድብ፥ ዘይ.) እግሩ ወይም ጫማው በፊና ሸፋፋ የሆነ (ሰው)።

ካብ "ካበ" ስር ተመ.

ካቦ¹ ስ አራት ቁና የሚይዝ መስፈሪያ።

ካቦ² ስ ትልቅ የሆነ የዋንጫ ወይም የፅዋ አይነት።

ካቦ ስ በህንፃ፥ በመንገድ፥ በፋብሪካ፥... ስራ ላይ የሚሰማሩ የጉልበት ሰራተኞችን እንደአለቃ ሆኖ የሚያሰራ ሰው።

ካቦርት (ካቦርታ፥ ካፖርት) ስ ከማንኛውም ልብስ በላይ ተደርቦ የሚለበስና ለብርድ መከላከያ የሚያገለግል ረጅም ኮት።

ካቲ ስ ከተረከዝ ከፍ ብሎ የሚገኝና ለብቻው ቀጥ ብሎ የሚታይ ወፍራም ጅማት።

ካቲካላ ስ በፋብሪካ ሳይሆን በመኖሪያ ቤት ውስጥ የሚዘጋጅ የአልኮል መጠጥ።

ካታሎግ ስ 1.በፊደል ተራ በካርድ ላይ የተመዘገበ የማንኛውም ነገር ዝርዝር። 2.በአይነት፥ በመጠን ወይም በሚሰጡት ግልጋሎት፥... መሰረት ለምርጫ እንዲያመች ሆኖ የተዘጋጀ የእቃዎች፥ የልብሶች፥ የቦታ፥ የስሞች፥ ... ዝርዝር ያለበት ወረቀት፥ ጥራዝ ወይም መፅሃፍ።

ካቴና ስ 1.ሰንሰለት። 2.በሰንሰለት ቅርፅ ከወርቅ የሚሰራና እጅ ላይ የሚደረግ ጌጥ። 3.ሁለት ትልልቅ የብረት ቀለበቶችን በሰንሰለት በማገናኘት የተሰራና የእስረኛን እጅ ወይም እግር ለማሰር የሚያገለግል ሰንሰለት።

ካቴድራል ስ ደረጃው ወይም ማእረጉ ከፍተኛ የሆነ ታላቅ ቤተ ክርስቲያን፤ ርእሰ አድባራት፥ ገዳም።

ካትራሜ ስ ሬንጅ።

ካቶሊክ ስ 1.የሮማ ቤተክርስቲያን እምነት። 2.የካቶሊክ እምነት ተከታይ፡

ካቻምና "ሃች አምና"ን ተመ.

ካነ ግ 1.የድቁና ወይም የቅስና ስልጣን ሰጠ፥ ሾመ፤ ክህነት ሰጠ። 2.አስተማረ፥ አሰለጠነ።

ካህን (ብ.ቁ.ካህናት) ስ በቤተ እግዚአብሄር ለማገልገል የሃይማኖት ትምህርትና ስልጣን ያለው መንፈሳዊ አገልጋይ፥ አስተማሪ።

ክህነት ስ ሃይማኖታዊ ስልጣን።

ክህነት ተቀበለ የቅስና ወይም የድቁና ስልጣን (ማእረግ) አገኘ።

ተካነ ግ 1.ክህነት ተቀበለ። 2.ሰለጠነ፥ በደምብ አወቀ።

ካናቴራ(ካኒቴራ) ስ ከክር ወይም ከናይለን ወይም ከጥጥ፥... የሚሰራ ከወገብ በላይ የሚለበስ የውስጥ ልብስ።

ካንሰር ስ የማይድንና አደገኛ የሆነ፥ ብዙውን ጊዜ ሞት የሚያስከትል በሽታ።

ካንዴላ ስ እሳት በመርጨት የመኪናው ሞተር እንዲነሳ የሚረዳ የመኪና እቃ።

ካንጋሩ ስ ለመዝለል የሚያስችሉ ጠንካራ የሆኑ የኋላ እግሮች ያሉት፥ በአውስትራሊያ ብቻ የሚገኝ የዱር እንስሳ። ሴቷ ካንጋሩ ልጇን ለመሸከም የሚያስችላት ከረጢት መሰል አካል በስተውጪ በኩል በሆዷ ላይ አላት(ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።

ካእብ ስ እንደ ሁ፥ ሉ፥ ሙ፥ ... ያሉ በግእዝና በሳልስ ፊደላት መካከል የሚገኙ ሁለተኛዎቹ የፊደላት ዘሮች መጠሪያ ወይም የድምፅ ምልክቶች።

ካከመ ግ ዛለ፥ ደከመ፥ ጣመነ።

ካከረ ግ ጠነከረ።

ካክራ ቅ ጠንካራ፤ ብርቱ።

ካኪ ስ በአይነቱ ከአቡጀዲና ከመርደፋ ሻልና ጠንከር ብሎ በተለያዩ ቀለማት ከጥጥ የሚሰራ የጨርቅ አይነት።

ካኪ መልክ/ቀለም የመዳብ ወይም የነሃስ ወይም የአፈር መልክ ያለው ቀለም።

ካኪሳ ስ በጣም ያላደገና ያልጠነከረ አደገኛ አዳኝ ዘንዶ።

ካካ (አካካ) ስ 1.ኩስ፥ አይነምድር። 2.ቆሻሻ፥ መጥፎ (ለልጆች ወይም ከልጆች የሚነገር)።

*ካካ

ካካቴ ቅ ሳቂታ።

ተንካካ ግ 1.ከመውደቅ ወይም ከመጋጨት የተነሳ የሚንኳኳ ድምፅ ሰጠ። 2.እንደ ብርጭቆ፥ ጠርሙስ፥ ሸክላ፥ ... ያለ እቃ ተደራርቦ ሲወድቅ የሚያሰማውን አይነት ድምፅ ሰጠ ወይም አሰማ። 3.ሳቀ፥ ተንከተከተ።

አንካካ ግ 1.አሳቀ፥ አንከተከተ። 2.እንደ ብርጭቆ፥ ጠርሙስ፥... ያሉ እቃዎችን አተራመሰ፥ አጋጨ።

አስካካ (አሽካካ) ግ 1.እየጮሀ ሳቀ። 2.ጮሀ (ፈረስ)። 3.ሳቅ የሚመስል የጩሀት ድምፅ አሰማ (ጅብ በስረያ ጊዜ)።

ካካቲ¹ ስ የአሪባራ ሌላ ስም።

ካካቴ² "***ካካ**" ስር ተመ.

ካክራ "**ካከረ**" ስር ተመ.

ካውያ ስ የልብስ መተኮሻ።

ካዝና ስ እንደ ብር፥ ወርቅ፥ ገንዘብ፥... ያሉ ውድ ንብረቶች የሚቀመጡበት የብረት ሳጥን።

ካይንት ስ የዝይ ሌላ ስም።

ካደ ግ 1.ሃይማኖቱን ተወ፥ ለወጠ። 2.አሌ አለ፥ ሸፈጠ። 3.ውል፥ ቃል ኪዳን አፈረሰ ወይም ጣሰ። 4.ለየ፥ አገለለ፥ ያለውን የስጋ ዝምድና ትስስር ሰረዘ።

ከሃዲ ቅ 1.ቃሉን የሚያጥፍ፥ እምነት የማይጣልበት። 2.ሃይማኖቱን የካደና የገዛ ሃይማኖቱ ተቃዋሚ የሆነ።

ክህደት (ክደት) ስ 1.የእምነት ተቃራኒ። 2.ሸፍጥ።

ካደመ ግ አገለገለ (ቡና በማፍላት)።

ካዳሚ ቅ በባህላዊ መንገድ ቡና አፍልቶ ለጠጪዎች የሚያድል።

ካድሬ ስ በመንግስታዊ ተቋም፥ በፓርቲ፥ በሙያ ማህበራትና በህዝባዊ ድርጅቶች ውስጥ በተወሰነ የስራ መስክ የተመደበና ለተመደበበትም ስራ የሰለጠነ ሰራተኛ። በጦር ሃይሎች ውስጥ በቋሚ ስራ ላይ የሚገኙ መኮንኖችና የበታች ሹማምንትም ካድሬዎች ተብለው ይጠራሉ።

*ካፈፈ (*ኳፈፈ)

ተንካፈፈ (ተንኳፈፈ) ግ ተንሳፈፈ።

አንካፈፈ (አንኳፈፈ) ግ አንሳፈፈ።

ካፈር "**ካፍር**"ን ተመ.

ካፌቴሪያ ስ ተመጋቢዎች ራሳቸውን የሚያስተናግዱበት ምግብ ቤት ወይም ሆቴል።

*ካፋ

ካፊያ ስ በጣም ቀላል የሆነ ዝናብ (ብዙውን ጊዜ ዝናብ መዝነብ ሲጀምር ያለው አይነት ዝናብ)።

አካፋ ግ ካፊያ ጣለ።

ካፍር (ካፈር) ስ በቡቅሉ ከንፈር ላይ የሚወጣ የበሽታ አይነት።

ካፒታሊስት ስ 1.በካፒታሊስት ስርአተ ማህበር መርህ የሚተዳደር አገር። 2.የካፒታል ባለቤት።

ካፒታሊዝም ስ የአንድ አገር ንግድ፥ ኢንዱስትሪ፥... በባለሃብቶች የግል ይዞታ ስር ሆኖ የሚንቀሳቀስበት የኢኮኖሚ ስርአት።

ካፒታል ስ ትርፍ እንዲያስገኝ በንግድ፥ በምርት፥... ስራ ላይ የዋለ ወረት፥ ገንዘብ።

ካፒቴን ስ አለቃ፥ አዛዥ (የመርከብ፥ የአይሮፕላን፥...)።

ካፖርት "**ካቦርት**"ን ተመ.

ኬ የ"ከ" ፊደል ሃምስ ዘር።

ኬላ ስ የይለፍ ወይም የፈቃድ ወረቀት የያዙ ሰዎችና በህጋዊነት ሊገቡ ወይም ሊወጡ የሚችሉ እቃዎች የሚተላለፉበት፥ ይህንኑ ተግባር እንዲቆጣጠሩ በተመደቡ ሰዎች የሚጠበቅ የአገር ውስጥ መንገድ ወይም የጠረፍ በር።

ኬላ ሰበረ አስፈላጊውን የይለፍ ወይም የፈቃድ ወረቀት ሳይዝ በህግ ወጥ መንገድ ኬላን አልፎ ሄደ።

ኬላ ተሰበረ በሰርግ ጊዜ ልጃገረድ ድንግልናዋ ከተገሰሰ በኋላ የሚባል የሰርግ ዘፈን።

ኬሚስት ስ በኬሚስትሪ የሰለጠነ ሰው።

ኬሚስትሪ ስ ልዩ ልዩ ንጥረ ነገሮች ከምን እንደተሰሩ፥ እርስ በእርሳቸው እንዴት ሊዋሃዱ እንደሚችሉና በተለያዩ ሁኔታዎች ጊዜ ምን አይነት ጠባይ እንደሚያሳዩ የሚያጠና የሳይንስ ዘርፍ።

ኬሚካል ስ ለኬሚስትሪ ስራ የሚውል ወይም የኬሚስትሪ ስራ ውጤት የሆነ ንጥረ ነገር።

ኬማ ስ የዶማ ወይም የማረሻ እላቂ ብረት።

ኬሻ ስ ከቄጠማ ወይም ከዘንባባ ወይም ከእንሰት፥... የሚሰራ ምንጣፍ ወይም ከረጢት።

ኬብል ስ በምድር ወይም በባህር ውስጥ የስልክና የቴሌግራም መልእክቶችን እንዲያስተላልፍ የተቀበረ የሽቦዎች ስብስብ።

ኬንትሮስ ስ በዲግሪ የሚለካና ከግሪንዊች ወደ ምስራቅ ወይም ምእራብ አቅጣጫ ያለ የቦታ ርቀት።

ኬክ ስ ከዱቄት፣ ከእንቁላል፣ ከቅቤ፣ ከስኳር፣... ተዘጋጅቶ የሚጋገር ጣፋጭ ምግብ።

ኬክሮስ ስ በዲግሪ የሚለካና ከምድር ወገብ ወደሰሜን ወይም ወደ ደቡብ አቅጣጫ ያለ የቦታ ርቀት።

ክ የ"**ከ**" ፊደል ሳድስ ዘር።

-ክ "**-ህ**"ን ተመ.

ክህነት "**ካነ**" ስር ተመ.

ክህደት "**ካደ**" ስር ተመ.

ክለሳ "**ከለሰ**" ስር ተመ.

ክለብ "**ከበበ**" ስር የ "**ክበብ**"ን 1ኛና 2ኛ ፍቺ ተመ.

ክሊኒክ ስ ብዙውን ጊዜ ተመላላሽ ታካሚዎችን እየተቀበለ የሚያክም አነስተኛ የህክምና ተቋም።

ክሳ "**ከሳ**" ስር ተመ.

ክላርኔት ስ ሙዚቃዊ የድምፅ ስልቶችን ለማውጣት የሚረዱና በጣት የሚነኩ ቁልፎች ያሉት በትንፋሽ የሚሰራ ዋሽንት መሳይ ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያ(ስእሉን የሙዚቃ መሳሪያ ስር ተመ.)።

ክላሰር ስ ልዩ ልዩ የማስረጃ ሰነዶች የሚያዙበት ወፍራም ወረቀት፤ ዶሴ።

ክላሲካል ሙዚቃ ስ 1.ከጥንት ጀምሮ የኖረና ዘመን አመጣሽ ያልሆነ ረቂቅ የሙዚቃ ጥበብ። 2.ድምፃዊ ሳይኖርበት በመሳሪያ ብቻ የተቀነባበረ ሙዚቃ።

ክላክስ ስ የመኪና ጥሩንባ።

ክልል "**ከለለ**^{1}" ስር ተመ.

ክልስ "**ከለሰ**^{2}" ስር ተመ.

ክልብልብ "**ከለበ**" ስር ተመ.

ክልብሽ

ክልብሽ አለው ግ አቅለሸለሸው።

ክልትው

ክልትው አለ ግ ከድካም፣ ከመዛል፣... የተነሳ ወደቀ፣ ተዘረረ፤ ተኛ።

ክልትው አደረገ ግ ጣለ።

ክልክል "**ከለከለ**" ስር ተመ.

ክልፍልፍ "***ከለፈ**" ስር ተመ.

ክምር "**ከመረ**" ስር ተመ.

ክምችት "***ከመቸ**" ስር ተመ.

ክረምት ስ ከሰኔ 26 እስከ መስከረም 25 ድረስ ያለው የዝናብ ወራት ወይም ጊዜ።

ክረምት አግቢ (አግባ) ስ በክረምት መግቢያ ሰሞን ከመሬት ውስጥ በብዛት የሚፈላ በራሪ ነፍሳት፣ አሸን፣ ምስጥ።

ክሪክ ስ የመኪና ጎማ በሚቀየር ጊዜ ወይም ሌላ ጥገና ማድረግ ሲያስፈልግ የመኪናውን አካል ወደ ላይ ለማንሳት የሚጠቅም መሳሪያ።

ክራር ስ ባለስድስት አውታር (ክር) ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያ(ስእሉን የሙዚቃ መሳሪያ ስር ተመ.)።

ክራሞት "**ከረመ**" ስር ተመ.

ክራባት (ከረባት) ስ ቀጠንና ረዘም ተደርጎ ከጨርቅ ወይም ከቆዳ የሚዘጋጅ፣ በአንገት ላይ ከሸሚዝ ኮሌታ ስር የሚታሰርና በደረት ላይ ቁልቁል የሚንጠለጠል ወይም በአጭሩ በቢራቢሮ ቅርፅ ተዘጋጅቶ በስተፊት በኩል በሸሚዝ ኮሌታ ላይ የሚደረግ የሸሚዝ ማስጌጫ።

ክራንቻ (የውሻ ክራንቻ) ስ በፊት ጥርስና በመንጋጋ መካከል ከላይና ከታች በኩል ግራና ቀኝ የሚገኙ፣ ቀጠንና ሾል ያሉ አራት ጥርሶች(ስእሉን ጥርስ ስር ተመ.)።

ክራንቻ ጥርስ ዝ.ክ.

ክራይ "***ከረየ**" ስር ተመ.

ክር "**ከረረ**" ስር ተመ.

ክርስቲያን የክርስትና ሃይማኖት ተከታይ።

ክርስትና ስ 1.የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት በመቀበል ወይም በማመን ላይ የተመሰረተ ሃይማኖት፤ የክርስትና እምነት። 2.አንድ ሰው የክርስትና ሃይማኖት አባል በሚሆንበት ጊዜ በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚፈፀምለት ስርአተ ጥምቀት።

ክርስትና ተነሳ የክርስትናን እምነት ተቀበለ፤ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ተጠመቀ።

ክርስትና አነሳ አንድ ሰው በጥምቀት አማካይነት የቤተክርስቲያን አባል በሚሆንበት ጊዜ በስርአቱ ላይ ተገኝቶ ቃልኪዳን በመግባት የተጠማቂው ሰው የክርስትና አባት ሆነ።

ክርስትና ልጅ ስ ለክርስትና አባት ወይም እናት በቃል ኪዳን የተሰጠ የሃይማኖት ወይም የጥምቀት ልጅ።

ክርስትና አባት ስ ወንድ ልጅ በሚጠመቅበት ጊዜ ሃይማኖትን ሊያስተምረው ቃል ገብቶ ሃላፊነትን የሚወስድ የቃል ኪዳን ወይም የሃይማኖት አባት።

ክርስትና እናት ስ ሴት ልጅ በምትጠመቅበት ጊዜ ሃይማኖትን ልታስተምራት ቃል ገብታ ሃላፊነቱን የምትወስድ የቃል ኪዳን ወይም የሃይማኖት እናት።

የክርስትና ስም ስ አንድ ህፃን ወይም ትልቅ ሰው ሲጠመቅ ወይም ክርስትና ሲነሳ በቀሳውስት

የሚሰጠው ሃይማኖታዊ ስም።

ክርስቶስ ስ የኢየሱስ የተቀባእ (የሹመት) ስም ሲሆን፥ ብዙ ጊዜ ከስሙ ጋር ተጣምሮ ኢየሱስ ክርስቶስ ወይም ለስሙ (ለኢየሱስ) እንደተለዋጭ ስም ሆኖ ያገለግላል።

ክርታስ ስ 1.መፃፊያ ወረቀት ወይም ብራና። 2.ለእቃ መያዣ፣ ... እንዲሆን በኪስ፣ ሳጥን፣ ... መልክ ተደርጎ የሚሰራ ወፍራም ወረቀት፤ ካርቶን። 3.በማህፀን ውስጥ ያለ ሽል የሚጠቀለልበት ብራና መሰል ስስ ቆዳ፤ ሰፋድል።

ክርትስ "ከረተሰ" ስር ተመ.

ክርትፍ "ከረተፈ" ስር ተመ.

ክርን "ከረና" ስር ተመ.

ክርካር ስ በኪራይ ለተወሰደ ከብት የሚከፈል የጉልበት ዋጋ።

ክርክራት "ከረከረ" ስር "ክርክር"ን ተመ.

ክርክር "ከረከረ" ስር ተመ.

ክርኸር "*ከረኸረ" ስር ተመ.

ክርክሮሽ "ከረከረ" ስር ተመ.

ክርድድ "ከረደደ" ስር ተመ.

ክርፋታም "ከረፋ" ስር ተመ.

ክርፋት ዝ.ክ.

ክሰል "ከሰለ" ስር "ከሰል"ን ተመ.

ክሳት "ከሳ" ስር ተመ.

ክሳድ ስ 1.በማጅራት በኩል ያለ የአንገት ክፍል። 2.አንገትጌ።

ክስ[1] "ከሰሰ" ስር ተመ.

ክስ[2] ፍየልንና በግን ሂድ ወይም ወግድ ለማለት የሚባል ቃል።

ክስል "ከሰለ" ስር ተመ.

ክስረት "ከሰረ" ስር ተመ.

ክስተት[1] ስ ከዳዊት መዝሙር ተውጣጥቶ የተቀናበረ ያሬዳዊ የዜማ ድርሰት።

ክስተት[2] "ከሰተ" ስር ተመ.

ክስካስ ስ የጭነት ከብት ሆዱ እንዳይጎዳ ከኮርቻ ወይም ከጭነት ስር የሚደረግለት ድልዳል።

ክስካሽ "ከሰከሰ" ስር ተመ.

ክስክስ ዝ.ክ.

ክሽን "ከሸነ" ስር ተመ.

ክሽክሽት (ክሽክሽ) ስ 1.ጤፍ የሚያከክልና ጎመን ላይ የሚገኝ የጎመን ትል። 2.ነጭ የጆሮ እከክ።

ክበብ "ከበበ" ስር ተመ.

ክበድ "ከበደ" ስር ተመ.

ክቡራት "ክብርት"ን ተመ.

ክቡራን "ክቡር"ን ተመ.

ክቡር (ብ.ቁ.**ክቡራን**፥ አን. **ክብርት**፡ አን. ብ.ቁ.**ክቡራት**) ቅ 1.በከፍተኛ ደረጃ ላይ ለሚገኝ ባለስልጣን የሚቀርብ የማእረግ መግለጫ ቃል። *ክቡር ሚኒስትር/ክቡር ላቀ አገሌ።* 2.የአክብሮት መግለጫ ቃል። *ክቡር ወንድሜ ሆይ።*

ክቢ

ክቢ ሰራው ጉድ አደረገው።

ክባስ "ከበሰ" ስር ተመ.

ክብ "ከበበ" ስር ተመ.

ክብረ ሰማይ ስ. ሰዎች ለቁስል መድሃኒት ይሆናል ብለው የሚጠቀሙበት የማእድን አይነት።

ክበረ በኣል "ከበረ" ስር ተመ.

ክብረ ነክ ዝ.ክ.

ክብረ ነገስት ዝ.ክ.

ክብረ ንፅህና ዝ.ክ.

ክብረ ወሰን ዝ.ክ.

ክብረት ዝ.ክ.

ክብሪት ስ 1.ከክብሪት ቤት ላይ ወይም ሻካራ ነገር ላይ ሲጭሩት እሳት የሚሰጥ ማእድን የተጣበቀበት አነስተኛ እንጨት ከነመያዣው። 2.(ዘይ.) ነገር ኣያያዥ።

ክብሪት ጫረ የክብሪትን እንጨት ለዚሁ ተብሎ ከተዘጋጀና ሻካራነት ካለው ነገር ጋር በማፋተግ እሳት አያያዘ።

የክብሪት ቤት ስ ከጠንካራ ወረቀት ወይም ፕላስቲክ፣... በሳጥን ቅርፅ (በውስጡ የክብሪት እንጨቶችን እንዲይዝና ውጫዊ ክፍሉ ደግሞ ክብሪትን ለመጫር እንዲያገለግል ሆኖ) የተሰራ መጠኑ አነስተኛ የሆነ የክብሪት መያዣ።

የክብሪት እንጨት ስ በአንደኛው ጫፉ ላይ እሳት የሚሰጥ ማእድን የተጣበቀበት ቀጭንና ትንሽ እንጨት።

ክብር "ከበረ" ስር ተመ.

ክብርት "ክቡር"ን ተመ.

ክብርና "ከበረ" ስር "ክብረ ንፅህና"ን ተመ.

ክብስብስ "*ከበሰበሰ" ስር ተመ.

ክብካቤ "ከበከበ" ስር "እንክብካቤ"ን ተመ.

ክብደት "ከበደ" ስር ተመ.

ክታብ "ከተበ[1]" ስር ተመ.

ክታች "ከተተ" ስር ተመ.

ኮት ዝ.ክ.

ኮትር "ከተረ" ስር ተመ.

ኮትባት "ከተበ^{2}" ስር ተመ.

ኮትካች "ከተከተ" ስር ተመ.

ኮትኮታ ስ ለአጥር፣ ለዱላ፣... የሚያገለግል፣ በለጋነቱ ደጋግሞ ተቀጥቅጦ መብራት ሊሆን የሚችልና ጥንካሬ ያለው አነስተኛ የዛፍ አይነት።

ኮትፍትፍ "*ከተፈ" ስር ተመ.

ኮትፎ "ከተፈ" ስር ተመ.

ኮችሌ ስ እንደ ጥቁር ሰሌዳ ለፅሁፍ የሚያገለግል ጠፍጣፋ ድንጋይ።

ኮቾ "ከቸቸ" ስር ተመ.

ኮናድ "ከነዳ" ስር ተመ.

ኮንብንብ "*ከነበ" ስር ተመ.

ኮንኮና ስ በበርበሬ ዛላ ውስጥ ፍሬውን የሚሸከመው ክፍል።

ኮንዋኔ "*ከነወነ" ስር ተመ.

ኮንውን ዝ.ክ.

ኮንድ "ከነዳ" ስር ተመ.

ኮንፍ "ከነፈ" ስር ተመ.

ኮኮ "ከካ" ስር ተመ.

ኮው አለ^{1} ግ በጣም ደነገጠ።

ኮው አለ^{2} ግ በጣም ደረቀ (በፀሃይ)።

ኮው አለ^{3} ግ ጮኸ፤ ኪው አለ (ደወል፣ ቆርቆሮ)።

ኮዳን "ከደነ" ስር ተመ.

ኮጂላ "ከጀለ" ስር ተመ.

ኮፈፍ "ከፈፈ" ስር ተመ.

ኮፉ "ከፋ" ስር ተመ.

ኮፉኛ ዝ.ክ.

ኮፉት ዝ.ክ.

ኮፉይ "ከፈለ" ስር ተመ.

ኮፍል ዝ.ክ.

ኮፍልፋይ ዝ.ክ.

ኮፍልፍል ዝ.ክ.

ኮፍትት "ከፈተ" ስር ተመ.

ኮፍት አፍ ዝ.ክ.

ኮፍት ዝ.ክ.

ኮፍኮፋት "ከፈከፈ" ስር ተመ.

ኮፍኮፍ ዝ.ክ.

ኮፍያ "ከፈለ" ስር ተመ.

ኮ ተ "**ከ**" ፈደል ሳብእ ዘር።

ኮለለ^{1}

ኮለል (ኩልል) አለ ግ 1.ቀስ እያለ ወረደ፣ ፈሰሰ (ፈሳሽ)። 2.እየተንከባለለ፣ እየተሽከረከረ ሄደ (ብዙውን ጊዜ ድቡልቡል ወይም ክብ ነገር)።

ተንኳለለ ዝ.ክ.

***ኮለለ^{2}**

ኮለል (ኩልል) አለ ግ ወለል ወይም ጥርት ብሎ ታየ። *ኮለል ያለ ውሃ ኩልል ያለች ፀሃይ።*

ኮለሌ ስ ከቆዳ ለተሰራ ሚዛን ማንጠልጠያና እንደ ክብደት መጠን መለኪያ ሆኖ የሚያገለግል እንጨት።

ኮለል ስ 1.የወንድ አባለዘር ጫፍ። 2.የተጠረበና የተላገ ክርሙልሙል የበር መቀርቀሪያ እንጨት። 3.የሞፈር ቂጥ። 4.ድብልብል የሚዛን ድንጋይ፣ እንደኪሎ ያለ መለኪያ። 5.ወናፍን ከመደብ (ከወፍራሙ የወናፍ ቧንቧ) ጋር የሚያገናኘው ቀጭን የብረት ቧንቧ።

***ኮለተፈ**

ኮልታፋ (ኩልትፍ) ቅ አፉን እንዳልፈታ ህፃን የሚናገር፣ ተብታባ።

ተኮለታተፈ ግ አፉን እንዳልፈታ ህፃን አድርጎ ተናገረ፣ ተንተባተበ።

ተኮላተፈ ዝ.ክ.

አኮለታተፈ ግ አፉን እንዳልፈታ ህፃን አድርጎ ተናገረ፣ ተንተባተበ።

አኮላተፈ ዝ.ክ.

ኮለኮለ^{1} ግ በአንድ ቦታ በብዛት ሰበሰበ፣ አከማቸ፣ ደረደረ።

መኮልኮያ ስ በቤተ መንግስት በር ላይ የሚገኝ አደባባይ (ሰዎች ግብር ለመብላት ተራ የሚጠብቁበት)።

ኮልኮሌ ቅ ቅራቅንቦ፣ ኮተት።

ተኮለኮለ ግ ተሰበሰበ፣ ተደረደረ፣ ተከማቸ።

ኮለኮለ^{2} ግ የ"**ኮረኮረ**"ን 1ኛና 2ኛ ፍቺ ተመልከት።

ኮለፈ ግ በጭቃ፣ በደም፣ በወጥ፣... በከለ፣ አበላሸ (ልብስን፣ አካልን)።

ኩልፍልፍ ቅ የተበከለ፣ የተበላሸ (በጭቃ፣ በደም፣ በወጥ፣...)።

ኮሳ^{1} ግ የቆሸሸ ወይም መልኩ የደበዘዘ ወርቅን፣ ብርን፣ ነሃስን፣ ... በኮመር አፀዳ፣ ቦረሸ፣ ወለወለ። 2.ብር ወይም ወርቅ ያልሆኑ የጌጥ እቃዎችን፣ ብር ወይም ወርቅ እንዲመስሉ ብር ወይም ወርቅ ቀባ።

ኮሳ^{2} ስ እንደሙቅና ሙጫ ያለ ማጣበቂያ።

***ኮሳሸ**

ኩልሽ ቅ አባለ ዘሩ የተቀጠቀጠ (በሬ፣ በግ፣...)።

ተኮላሸ ግ 1.ተቀጠቀጠ (የወንድ አባለ ዘር)። 2.ተሰናከለ፣ ተጨናገፈ።

አኮላሸ ግ ቀጠቀጠ (የወንዱን አባለ ዘር)። 2.አሰናከለ፣ አጨናገፈ።

ኮሌታ ስ አንገትጌ።

ኮሌጅ ስ ልዩ ልዩ የሙያ ወይም ከፍተኛ ትምህርት የሚሰጥበት የትምህርት ተቋም።

ኮልባ ስ 1.ከጎሽ ወይም ከበሬ፣ ... ቀንድ የሚሰራ ዋንጫ። 2.ከቀንድ የሚሰራ የጎራዴ ወይም የቢላዋ እጀታ። 3.ከጎሽ ቀንድ የሚሰራ ሎቲ ወይም ቀለበት።

ኮልባቋሬ ስ የውስጠኛውና የላይኛው ክፍል የተለያየ መልክ ያለው የካባ ጨርቅ።

ኮልታፋ "*ኮለተፈ" ስር ተመ.

ኮልኮሌ "ኮለኮለ^1" ስር ተመ.

ኮሎኒያሊስት ስ ቅኝ ገዥ።

ኮሎኒያሊዝም ስ ቅኝ አገዛዝ።

ኮሎኔል ቅ ከሌተናል ኮሎኔል በላይ ከብርጋዴር ጄኔራል በታች ያለ የወታደራዊ ማእረግ ስም።

ኮመረ

ኮመረች ግ እንደ ጠላ፣ ያገር አረቂ፣ ጠጅ፣... ያሉትን መጠጦች እያዘጋጀች ሸጠች።

ኮማሪ (ኮማሪት) ቅ እንደጠላ፣ ያገር አረቂ፣ ጠጅ፣ ... ያሉትን መጠጦች የምትሸጥ ሴት።

ኮመር ስ 1.ለነሃስ፣ ለብር፣... ጌጣጌጦች ማሳመሪያ ወይም ማደሻ የሚያገለግል በአንድነት የፈላ የጨው፣ የባሩድ፣ የድኝ፣ የእንቆቆ ድብልቅ። 2.እንደ ብር፣ ወርቅ፣... ያሉትን የጌጥ እቃዎች ለማደስ ወይም ለማሳመር የሚያገለግል የኬሚካል አይነት።

***ኮመተረ**

ኮምታራ ቅ 1.ጨምዳዳ፣ ጨምታራ።2.ኮስታራ።

ኮምታሬ ስ በጣም የከረረ የድር አይነት።

ኩምትር አለ ግ 1.ጭምድድ፣ ጭምትር አለ። 2.ቆጥሮ፣ ኩስትር አለ (ፊት)።

ኩምትር አደረገ ግ 1.ጭምድድ፣ ጭምትር አደረገ። 2.ቆጥሮ፣ ኩስትር አደረገ (ፊትን)።

ተኮማተረ ግ 1.ጭምድድ፣ ጭምትር አለ። 2.ቆጥሮ፣ ኩስትር አለ (ፊት)።

አኮማተረ ግ 1.አጨማተረ። 2.ቆጥሮ፣ ኩስትር አደረገ (ፊትን)።

ኮመከ ግ 1.አስቂኝ የሆነ ድርጊት ፈፀመ (ሆን ብሎ)። 2.አሞኘ፣ ሸወደ፣ አታለለ (ለቀልድ)።

ኩምክና ስ አስቂኝ የሆነ ድርጊት።

ኮሚክ ቅ ቀልደኛ፣ አስቂኝ።

ተኮመከ ግ ተሞኘ፣ ተሸወደ፣ ተታለለ (በቀልድ)።

ኮመኮመ ግ 1.በሰፊው ተመገበ፣ ጠጣ። 2.ወሬን ለረዥም ሰአት አወራ ወይም አደመጠ።

ኮመጠጠ (ሆመጠጠ) ግ ሊጥ፣ ጠላ፣... ከመቡካት ወይም ብዙ ከመቆየት የተነሳ እንደ ሎሚ ኮስተር ያለ ጣእም አመጣ።

ኮምጣጤ (ሆምጣጤ) ስ 1.መጠኑና ቅርፁ እንደ ብርቱካን ያለ ሆኖ የሚኮመጥጥ ፍሬ የሚያፈራ የብርቱካን ዛፍን የሚያክል ተክል። ፍሬውም ኮምጣጤ ይባላል። 2. ከኮምጣጤ ፍሬ እየተዘጋጀ በሰላጣ ውስጥ የሚጨመር ፈሳሽ።

ኮሚሽነር ስ የኮሚሽን መስሪያ ቤት የበላይ ሃላፊ።

ኮሚሽን ስ 1.የተለያዩ ጉዳዮችን የሚያከናውንና ህጋዊ ስልጣን ያለው አካል። 2.እቃዎችን በማሻሻጥ፣ ጉዳይ በማስፈፀም፣... አገልግሎት ለሰጠ ግለሰብ ወይም ድርጅት የሚከፈል የአገልግሎት ዋጋ።

ኮሚቴ ስ ልዩ ልዩ ጉዳዮችን ለማከናወን ሌሎችን በመወከል ከብዙ ሰዎች መካከል የተመረጠ አካል ወይም ቡድን።

ኮሚኒስት ስ የኮሚኒዝም ፍልስፍና ወይም ርእዮተ አለም ተከታይ።

ኮሚኒዝም ስ የአንድ አገር ሃብትና የማምረቻ መሳሪያዎች በማህበረሰቡ የጋራ ይዞታ ስር የሚውሉበት ስርአተ ማህበር።

ኮሚክ "ኮመከ" ስር ተመ.

ኮማ ስ ከህመም ፅናት የተነሳ ራስን የመሳት ሁኔታ፣ ሻእር።

ኮማሪ(ት) "ኮመረ" ስር ተመ.

ኮሜዲ ስ አስቂኝ ድርጊቶች የሚታዩበት የድራማ አይነት።

ኮሜዲኖ ስ በተለያየ መጠንና ቅርፅ የሚዘጋጅ መሳቢያ፣ መደርደሪያ፣... ያለውና ለቤት እቃዎች (ሳህን፣ ብርጭቆ፣ ልብስ፣ ...) ማስቀመጫነት የሚያገለግል ባለመዝጊያ ቋሚ ሳጥን።

ኮምበር (ኮንበር) ስ ደንዳና ለምቦጭ።

ኮምታራ "*ኮመተረ" ስር ተመ.

ኮምታሬ ዝ.ክ.

ኮምጣጣ "ኮመጠጠ" ስር ተመ.

ኮምጣጤ ዝ.ክ.

ኮምፒዩተር ስ ልዩ ልዩ መረጃዎችን ለማጠናቀር እንዲሁም በተሰጠው መረጃ መሰረት ለተለያዩ ችግሮች መፍትሄ ለመፈለግና ሌሎች ማሽኖችን ለመቆጣጠር ወይም ለማሰራት

የሚያስችል በኤሌክትሪክ ሃይል የሚሰራ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያ።

ኮምፓስ^1 ስ ወደ ሰሜን በሚጠቆም መርፌው (ማግኔት) አማካኝነት እንደ ሰሜን፣ ... ያሉ አቅጣጫዎችን ለማመልከት የሚያገለግል መሳሪያ፣ መርሃ ሰሜን።

ኮምፓስ^2 ስ ክብ መስመር ለመስራት የሚያገለግል፥ በአንድ አፉ ሹል መርፌ በሌላ ጫፉ እርሳስ የሚሰካበት ዘንግ ያለው መሳሪያ።

ኮረመተ (ኮረተመ) ግ 1.አጠፈ፡ ጨበጠ (ሰውነትን)። 2. ጨመደደ፡ ጨበጠ።

ተኮረመተ ግ ተኮራመተ።

ተኮራመተ ግ 1.አጥፍ፡ ጭብጥ አለ (በአቀማመጥ፡ በአተኛኘት)። 2.(ዘይ.) በጣም ተቸገረ።

ኮረምቱ ስ የዝሆን አውራ።

ኮረሪማ ስ ሽፋኑ ጠንካራ የሆነና ፍሬው ለቅቤ ማንጠሪያ፡ ለወጥ፣... የሚሆን የቅመም አይነት።

ኮረሸመ (ኰረሸመ) ግ ከሽ ከሽ የሚል ድምፅ እያሰማ አኘከ (ቃሪያን፣ የእንጀራ ድርቆሽን፣...)።

ኮረብታ ስ ከአካባቢው መሬት ከፍ ብሎ የሚገኝ ስፍራ፡ አነስተኛ ተራራ፡ ጉብታ።

ኮረተ ግ 1.ከፍተኛ ባለው ግንብ መካከል ኮረትን ሞላ፡ ሰገሰገ (በግንብ ስራ ጊዜ)። 2.ተሰበሰበ፣ ተከማቸ። 3. አኮረተ።

ኮረት ስ አነስ አነስ ያለ ወይም የተሰባበረ ድንጋይ።

ኮረተመ "ኮረመተ"ን ተመ.

ኮረት "ኮረተ" ስር ተመ.

ኮረንቲ ስ 1.ኤሌክትሪክ። 2. (ዘይ.) ሃይለኛ። *ጠላዋ ኮረንቲ ነው።*

ኮረንቲ ጨበጠ በጣም ተናደደ።

ኮረከመ ግ 1.እጅን ጨብጦ ወይም ጣቶቹን አጥፎ በኩርኩም መታ፡ ገጨ (ጭንቅላትን)። 2.ከአንድ ነገር ላይ በመጠኑ ቀነሰ፡ አነሳ፡ ቆረሰ፡ ሸረፈ።

ኩርኩም ስ በታጠፉ የእጅ ጣቶች ጭንቅላት ላይ የሚደረግ ምት።

ኩርኳሚ ስ ያዋሲ ሽራፊ ወይም ስባሪ።

ኮረኮረ ግ 1.የብብትን አካባቢ በጣት ወጋ ወጋ አደረገ፡ ኮሰኮሰ (ለማሳቅ፣ ለማናገር)። 2.ከበቅሎ ወይም ከፈረስ ላይ የተቀመጠ ሰው የእንስሳውን አካል በተረከዙ ነካ ነካ፥ መታ መታ አደረገ፡ ኮሰኮሰ (ፍጥነቱን እንዲጨምር ለማድረግ)። 3.ጎተጎተ፥ ቀሰቀሰ፡ በነገር ነካካ (ለማናገር፣ ነገር ለማውጣጣት፥ ጠብ ለመጫር፥...)። 4.በጣት፣ በሳር፥ በሳባ፥... የጆሮን፣ የአፍንጫን፥... ውስጥ ነካካ፡ አከከ፣ ጎረጎረ። 5.አማሪትን ወይም የከበሮን ቂጥ እየደጋገሙ በስልት መታ።

ኮረኮሮ ስ በበጋ ወራት የሚፈጠር የዋልካ መሬት ስንጥቃት፥ ንቃቃት።

ኮረኮር^1 ስ የበግ ወይም የፍየል በጠጥ።

ኮረኮር^2 ስ ሌባ።

ኮረኮንች ስ 1.ጭንጫ ወይም ድንጋያማ መሬት። ቅ 2.በኮረት ወይም በድንጋይ ስብርባሪ የተሰራ (መንገድ)።

ኮረኳ ግ ነቀለ፥ መነገለ።

ኮረዳ ስ ለአቅመ ሄዋን የደረሰች ልጃገረድ።

ኮረጀ ግ የሌላን ሰው ስራ ወይም ሃሳብ የራሱ ስራ ወይም ሃሳብ እንደሆነ አድርጎ አቀረበ፤ ገለበጠ፤ ቀዳ።

ኩረጃ ስ ስርቆት (የእውቀት፥ የስራ)።

ኮረጆ ስ በተወሰነ ቁጥር ልክ እየሆነ በአንድነት የታሰረ የፍየል ወይም የበግ፥... የደረቀ ቆዳ።

ኮረጄ "ኮሮጄ"ን ተመ.

ኮረጠ "ሆረጠ"ን ተመ.

ኮረፈ ግ አረፋ አወጣ።

ኮረፎ ስ 1.አረፋ። 2.በድፍድፍ መልክ ተዘጋጅቶ የተቀመጠና አስፈላጊ በሆነ ጊዜ በውሃ ተበጥብጦ ጥቂት ከቆየ በኋላ የሚጠጣ አረፋነትና ጉሽነት ያለው ወፍራም ጠላ።

ተኮረፈረፈ ግ 1.አረፋ አበጀ። 2.ኩፍ አለ፥ አረፋ አበጀ፤ ፈላ።

***ኮረፈ**^{1}

ኩርፍ ቅ ጥል፥ ጥለኛ፡ ጠበኛ። *እከሊትና እከሌ ኩርፍ ናቸው።*

ኩርፈኛ ዝ.ከ.

ኩርፍታ ስ ኩርፊያ።

ኩርፍተኛ ቅ አኩራፊ።

ኩርፍታም ዝ.ከ.

ኩርፊያ ስ በመቀየም፥ በመከፋት፥ በመናደድ የተነሳ ንግግር ወይም ግንኙነት ማቆም።

ተኮራረፈ ግ ተቀያየመ፥ ከጠበኛው ጋር ንግግር፥ ግንኙነት አቆመ።

ተኳረፈ ዝ.ከ.

አኮረፈ ግ በጥል ወይም በሌላ ምክንያት ተቀይሞ ንግግር ወይም ግንኙነት አቆመ።

አኩራፊ ቅ በትንሽ በትልቁ የሚቀየም፥ የሚያኮርፍ።

አኮራረፈ ግ አቀያየመ፤ እንዳይነጋገሩ አደረገ፤ አጣላ።

አኳረፈ ዝ.ከ.

አስኮረፈ ግ አስቆጣ፡ አስቀየመ።

***ኮረፈ²**

ኩርፊያ ስ በእንቅልፍ ላይ እያለ የሚያንኮራፋ ሰው የሚያሰማው ድምፅ።

አንኮራፋ ግ በእንቅልፍ ላይ እያለ ጉሮሮ የአተነፋፈስ ድምፅ እያሰማ ተነፈሰ።

አንኳረፈ ግ.ከ.

***ኮረፈፈ**

ተንኮረፈፈ ግ አኮረፈ።

አንኮረፈፈ ግ አስኮረፈ።

ኮረፎ "*ኮረፈ" ስር ተመ.

ኮሪዶር ስ በቤት ውስጥ (ብዙ ጊዜ በክፍሎች መካከል) የሚገኝና ቀጠን ብሎ ረዘም ያለ ክፍት መተላለፊያ ቦታ።

ኮራ¹ ግ ታበየ፡ ታጀረ። 2.ተቆነነ፡ ተጀነነ። 3.ተመካ፡ ተማመነ። *የምኮራበት ወንድሜ ነው።*

ኩሩ ቅ 1.ጅንን፡ ቁንን። 2.ቁጥብ፡ ጨዋ። 3.ኩራተኛ።

ኩራት ስ 1.ትእቢት። 2.የመጀነን፡ የመኮፈስ ስሜት። 3.የንቀት ስሜት። 4.በአንድ ነገር ላይ መመካት ወይም አንድን ነገር አለኝታ ማድረግ።

ኩራተኛ ቅ 1.ትእቢተኛ። 2.ጅንን። 3.ሰው የሚንቅ።

ተኩራራ ግ 1. ተንቀባረረ። 2.ተማመነ፡ ተመካ። 3. ተበተ።

አኮራ ግ 1.አለኝታ ወይም መመኪያ ሆነ። *የሚያኮራ ዘመድ አለው።* 2.የደስታ፡ የአድናቆት፡ የርካታ፡ የክብር ስሜት እንዲፈጠር ምክንያት ሆነ። *አገሩን የሚያኮራ ስራ ሰራ።* 3.ትእቢተኛ አደረገ።

አኩራራ ግ የኩራት ስሜት ፈጠረ።

ኮራ² ግ ሸጠጠ፡ ተንቋጠጠ፡ ቀጢጥ አለ (የቤት ጣሪያ) የደራ ተቃራኒ።

ኮራ³ ግ በኮርኮም፡ በዱላ፡... ጭንቅላትን መታ።

ኮርማ ስ ያልተኮላሸና ልጅነት ያለው በሬ።

ኮርስ ስ 1.በተወሰነ ጊዜ የሚጠናቀቅ የተወሰነ የሙያ ወይም የቀለም ትምህርት ስልጠና (የጤና ረዳትነት፡ የፀሃፊነት፡...)። 2.በተወሰነ ጊዜ የሚጠናቀቅ የተወሰነ የቀለም ትምህርት (ኮሌጅ፡ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ)።

ኮርቤሳ ስ ያልተኮላሸና ልጅነት ያለው ፍየል፡ ወጠጤ።

ኮርቻ ስ 1.በበቅሎ፡ በፈረስ፡... ጀርባ ላይ ተደርጎ የሚታሰርና በላዩ ላይ ሰው የሚቀመጥበት ከእንጨት፡ ከቆዳ፡... የሚሰራ እቃ። 2.ብስኪሌት ጋላቢ የሚቀመጥበት የብስኪሌት ክፍል።

ኮርቻ አራገፈ ከፈረስ፡ ከበቅሎ፡ ... ጀርባ ላይ ኮርቻ አወረደ።



ኮርቻ (ም ፋ)

ኮርቻ ሰፊ ስ ኮርቻ ሰሪ።

ኮርቻ ትከሻ ስ የሱሪን ወገብር ወይም ዘቂጥ በኩል የሚወስደውን የሱሪ ጨርቅ አቀዳደድና አሰፋፍ ብቻ የሚመለከት ሲያፍ ቅድ።

የኮርቻ ኮብት ስ ለኮርቻ ጭነት ብቻ የተመደበና ሰው የማይጋልበት በቅሎ ወይም ፈረስ።

ኮርች ስ ግንዱ ከበሮ፡ ኮርቻ፡... ለመስራት የሚያገለግል እሾሃማ ዛፍ።

ኮርናፋ ቅ 1.ነፍናፋ። 2.ኩርፍተኛ።

ኮርፖሬሽን ስ በስሩ የተለያዩ ወይም ተመሳሳይ ስራ የሚያከናውኑ ድርጅቶችን የያዘ ትልቅ ድርጅት።

ኮሮጆ (ከረጆ) ስ እንደ ማህደር፡ አኮፋዳ፡ ስርሳ፡ ከረጢት ያለ የእቃ መያዣ።

ኮሰመነ ግ ኮሰሰ፡ ቀጠነ፡ መነመነ፡ ሰለለ፡ ጫጨ።

ኮስማና ቅ 1.(ሰው፡ ከብት) በጣም ቀጭን፡ ከሳሳ። 2.ቀጭን፡ ደቃቃ፡ አቅመ ቢስ።

ኮስረት ስ ለቅቤ ማንጠሪያ የሚያገለግልና ከሲ የሚመስል የተክል አይነት።

ኮሰሰ ግ 1.ከሳ፡ ኮሰመነ፡ በአካል አነሰ። 2.ደከመ፡ አቅመ ቢስ ሆነ።

ኮሳሳ ቅ 1.ከሲታ፡ ኮስማና። 2.አቅመ ቢስ።

ኮሰስ ብሎ ቀስ፡ ዝግ ብሎ።

አኮሰሰ ግ አናናቀ፡ አቃለለ፡ አንቋሸሸ።

አንኳሰሰ ግ.ከ.

ኮሰተረ¹ ግ 1.ተረከሰ፡ ለይቶ አስወገደ (የተቃጠለ የእንጨት፡ የሲጃራ፡ የጧፍ፡... ጫፍን)። 2.ጠረገ፡ አፀዳ። 3.ቆሰቆሰ፡ ወደ እሳት ገፋ፡ ጨመረ (በምድጃ ውስጥ ያለ እንጨት መንደዱን እንዳያቋርጥ)።

መኮስተሪያ ስ 1.መተርከሻ፡ የሲጋራ አመድ ማጠራቀሚያ። 2.መጥረጊያ።

ኩስታሪ ስ 1.የነደደ የጧፍ፡ የሲጃራ ክሳይ ወይም አመድ። 2.በርቶ ወይም ነዶ ያለቀ የጧፍ፡ የሻማ፡ የእንጨት፡... ትራፊ። 3.የቆሻሻ

ጥራጊ።

ኮሰተረ² ግ 1.ፈጀ፣ ተኮሰ፣ ለበለበ (በርበሬ)። 2.እንደመኮምጠጥ፣ እንደ መሾምጠር አለ (ጠላ፣...)። 3.ቋጠረ፣ አጠቆረ፣ አኮማተረ (ፊትን)። 4.ከወነ፣ ጠንቀቀ፣ ሰበሰበ (የተዝረከረከውን፣ የተንዘረፈፈውን፣... እቃ)።

ኮስታራ ቅ 1.ንቁ፣ ጥንቁቅ፣ ቀልጣፋ። 2.ሃይለኛ። 3.ዋዛ ፈዛዛ የማይወድ፣ ቁም ነገረኛ።

ተኮሳተረ ግ 1.ተቆጣ፣ ፊቱን አጠቆረ። 2.የሚያቃጥል፣ የሚፋጅ ወይም የሚለበልብ ሆነ (በርበሬ)።

አኮሳተረ ግ አስቆጣ፣ ከሰከሰ (ፊትን)።

ኮሰተረ³ ግ 1.አረመ፣ ኮተኮተ (አትክልትን)። 2.ቆፈረ።

ኮሰኮሰ ግ እንደማቅና በርኖስ ወይም እንደ አባጨጓሬ ያለ ነገር ሰውነትን ሲነካ የሚሰማውን አይነት ስሜት ተሰማ፣ ሸከረ፣ ሞረደ (ገላን)።

ኮስኳሳ ቅ 1.እንደበርኖስ ፀጉር የሚወጋ ወይም የሚሞርድ፣ ሻካራ። 2.(ዘይ.) አመለ መጥፎ፣ ነጭናጫ፣ ጠባዩ የማይመች።

ኮሲካሴ (አባ ኮስኳሴ) ስ አባ ጨጓሬ።

ኮሲ ስ 1.ቀፎ። 2.የቤት ጥራጊና የከብት ፋግ የሚፈስበት፣ በቤት አካባቢ የሚገኝ የዳበረ ቦታ ወይም መሬት።

ኮሳ ግ ኩሱን ጣለ፣ ተፀዳዳ (ዶሮ፣ አሞራ፣ ...)።

ኩስ ስ የዶሮ፣ የአሞራ፣... አይነ ምድር።

ኮሳሳ "**ኮሰሰ**" ስር ተመ.

ኮስማና "**ኮሰመነ**" ስር ተመ.

ኮስታራ "**ኮሰተረ²**" ስር ተመ.

ኮስኳሳ "**ኮሰኮሰ**" ስር ተመ.

ኮስኳሴ ዝ.ከ.

ኮሶ 1.በጥሬ ስጋ አማካይነት ከሰው ሆድ ገብቶ በመኖር ህመም የሚያስከትል ጥገኛ የትል አይነት። 2.ኮሶ የተባለውን ትል ከሆድ ውስጥ ለመግደል ወይም ለማስወጣት ተወቅጦና ተበጥብጦ የሚጠጣ መራራ ፍሬ። ፍሬውንም የሚያፈራው ዛፍ ኮሶ ይባላል።

ኮሶ ታየው /ተጋደደው/ ተጣባው የኮሶ ትል በሆዱ በመኖሩ ከአይነ ምድሩ ጋር ትሉ ወጥቶ ታየ።

ኮሶ ኮሶ አለው መረረው፣ ሰለቸው፣ አንገፈገፈው።

ኮሶ ፊት ፊቱ የማይፈታ፣ ፈገግታ የማይታይበት፣ ጨፍጋጋ ፊት።

የኮሶ ስንብት/መሰናበቻ ስ የኮሶ መድሃኒት ለጠጣ ሰው የሚሰጥ ወይም የሚዘጋጅ ምግብና መጠጥ ወይም ግብዣ።

ኮሶኛ ቅ የኮሶ መድሃኒት የወሰደ ወይም የጠጣ።

ኮሸለለ "**ከሸለለ**"ን ተመ.

ኮሸሻ (ኮሸሼ) ስ ግንዱም ቅጠሉም በሾክ የተሞላ የቁጥቋጦ አይነት።

ኮሸኮሸ ግ ሲያኝኩት ኮሽ ኮሽ የሚል ድምፅየሚሰጥ እንደ ቃሪያ፣ አገዳ፣ ... ያለን ነገር በላ ወይም ኮረሸመ።

ኮሽኮሺ ስ ሲያኝኩት ለጥርስ የሚገራ እንደ ፍርንባ፣ ... ያለና ኩርሽሚ የሆነ አጥንት።

ኮሽኮሽ ስ 1.ስስና አቅመቢስ የሆነ የአፍንጫ ወይም የሰርን አጥንት። 2.(ስድብ) ተልካሻ።

ኮሽ

ኮሽታ ስ ኮሽ የሚል አነስተኛ የድምፅ እንቅስቃሴ።

ኮሽ አለ ግ የደረቀ ቅጠል፣ ሳር፣ ... በነፋስ ወይም በሌላ ሃይል ሲንቀሳቀስ የሚሰጠውን አይነት ድምፅ ሰጠ ወይም አሰማ።

ኮሽ አይልም ምንም አይነት ድምፅ የለም ወይም አይሰማም፣ ፀጥ ያለ ነው።

ኮሽ ኮሽ አለ ግ ተንኮሻኮሸ።

ተንኮሻኮሸ ግ የደረቀ ቅጠል፣ ሳር፣... በነፋስ ወይም በሌላ ሃይል ሲንቀሳቀስ የሚሰጠውን አይነት ድምፅ ሰጠ ወይም አሰማ።

አንኮሻኮሸ ግ በመንቀሳቀስ ወይም በሌላ ሁኔታ ኮሽ ኮሽ የሚል ድምፅ እንዲፈጠር አደረገ።

ኮሻላ "**ከሸለለ**" ስር "**ኮሸለል**"ን ተመ.

ኮሽም ስ እሾህ ካለው የቁጥቋጦ አይነት የሚገኝ ፍሬው እንደ እንኩይ ያለ፣ ሲበስል ቢጫ የሚሆንና ሲበሉት በመጠኑ እንደመኮምጠጥ የሚል ፍሬ። ፍሬውን የሚያፈራው ተክልም ኮሽም ይባላል።

ኮሽታ "**ኮሽ**" ስር ተመ.

ኮበለለ ግ የነበረበትን ቦታ ትቶ ወደ ሌላ ቦታ ተደብቆ ወይም ተሸሽጎ ሄደ ወይም ጠፋ።

አኮበለለ ግ አስከድቶ ወሰደ።

አስኮበለለ ዝ.ከ.

ኮበሌ ስ ወጣት፣ ልጅ እግር፣ ጎረምሳ።

***ኮበኮበ**

ኩብ ስ 1.በኳስ ቅርፅ የተጠነጠነ ወይም የተጠቀለለ ፈትል፣ ክር፣...። 2. የ"**ኩብኩባ**"ን 1ኛ ፍቺ ተመ.

ኩብኩባ ስ 1.በአንበጣ የእድገት ኡደት ውስጥ ክንፍ አውጥቶ ከመብረሩ በፊት ያለው የግልገሉ አንበጣ መጠሪያ። 2.(ዘይ.) ወጣት።

አኮበኮበ ግ 1.ተንደረደረ፣ አቆበቆበ (ወደሰማይ ለመብረር)።2. ተዘጋጀ፣ ቃጣ፣ ተነሳ፣...(አንድን

ነገር ለማድረግ)።

ማኮብኮቢያ ስ በተለይ ለአውሮፕላን መነሻና ማረፊያ እንዲሆን በተዘጋጀ ቦታ ላይ አውሮፕላን መሬት እስከሚለቅ እንዲሁም ለማረፍ ሲፈልግ መሬት ነክቶ ወደመቆሚያው እስከሚደርስ በጎማዎቹ አማካይነት የሚንደረደርበት ረዥምና ሰፊ የሆነ መንገድ።

ኮባ ስ የእንሰት ተክል። ቅጠሉም ኮባ ይባላል።

ኮብሽ ስ ከጫማ እስከ ጉልበት ያለውን የእግር ክፍል የሚያደበለብል ወይም የሚያሳብጥ በሽታ፤ ከማን አንሺ።

ኮብሻም ቅ ኮብሽ የያዘው።

ኮተተ

ኮተት አለ ግ ተንኳተተ።

ኮተት አደረገ ግ አንኳተተ።

ተንኳተተ ግ 1.ቀስ እያለ ሄደ ወይም ተጓዘ። 2.ዳሀ፡ ተንፏቀቀ።

አንኳተተ ግ 1.ቀስ እያለ አጓዘ ወይም ወሰደ። 2.አንፏቀቀ።

ኮተቴ ስ ጥቁር የአደንጓሬ አይነት።

ኮተት ስ 1.ቅራቅንቦ፡ ግሳንግስ። 2.ብዙና የተለያዩ እቃዎች ባንድነት የሚጠሩበት ስም። 3.እድፍ፤ ጭቅቅት።

ኮተኮተ ግ አረምን ለማስወገድና አትክልቱን የለሰለሰ አፈር ለማስታቀፍ በአትክልቱ ዙሪያ ያለውን መሬት ቆፈር ቆፈር አደረገ።

መኮትኮቻ ስ ለኩትኳቶ ስራ የሚያገለግል መሳሪያ፤ አነስተኛ ዶማ፤...።

መኮትኮቻ

ኩትኮታ ስ ኩትኳቶ።

ኩትኳቶ ስ የመኮትኮት ተግባር።

ኮትኳች ቅ አትክልቶችን በማረምና በመ ኮትኮት የሚንከባከብ (ሰው)።

***ኮተኮተ**

ኩትኩት አለ ግ አኮተኮተ።

አኮተኮተ ግ 1.ሱክ ሱክ እያለ ቶሎ ቶሎ ተራመደ። 2.አቆበቆበ፤ ለመጀመር ተዘጋጀ። 3.አሳበቀ፤ አዋሸከ፤ ነገር ሰራ።

አኮትኳች ቅ አሳባቂ፤ አዋሻኪ፤ ነገር ሰሪ።

ኮታ ስ ለተወሰነ ወገን፤ ክፍል፤ ሰው፤... የሚሰጥ የተወሰነ የመጠን ወይም የቁጥር ድርሻ (በተለይ በአንድ የተወሰነ ጊዜና ሁኔታ ሊመረቱ ወይም ሊሸጡ የሚገባቸው እቃዎች ብዛት ወይም ለአንድ የተወሰነ ነገር የሚያስፈልጉ የሰዎች ወይም የሌላ ነገር ቁጥር፤ መጠን)።

ኮቴ ስ 1. መሬት የሚረግጠው የእግር ክፍል። 2. ከብት ወይም ሰው የረገጠው ለስላሳ ቦታ ላይ የሚቀረው ምልክት።

ኮት ስ በሸሚዝ ወይም በሹራብ ላይ የሚለበስ፤ ባለእጅጌ የሆነና ከፊት ለፊቱ ክፍት ሆኖ ቁልፍ ያለው።

ኮትቻ ስ መረሬ፤ ጥቁር አፈር፤ ዋልካ መሬት።

ኮትኳች "ኮተኮተ" ስር ተመ.

ኮቸመ ግ በጥንቃቄ ልቅምና ጥብቅ አድርጎ ሰራ (ብዙ ጊዜ የእጅ ስራን)።

ኮቸረ "ከቸረ"ን ተመ.

ኮቸሮ ዝ.ከ.

***ኮነሰነሰ**

ኩንስንስ ቅ ዝይን፤ ዘናጭ፤ ሽሙንሙን ሽቅርቅር (በአለባበስ፣ በአካላዊ አኳኋን)።

ኩንስንስ አለ ግ ተኩነሰነሰ።

ተኩነሰነሰ ግ ተዘየነ፡ ዘነጠ፡ ተሽሞነሞነ፡ ተሽቀረቀረ (በአለባበስ፣ በአካላዊ አኳኋን)።

አኩነሰነሰ ግ ዘየነ፤ አሽሞነሞነ፡ አሽቀረቀረ (በአለባበስ፣ በአካላዊ አኳኋን)።

***ኮነተረ**

ተሸኮነተረ ግ አጌጠ፡ ተዋበ፡ አማረ።

ተሸኮንታሪ ቅ ሽቅርቅር።

አሸኮነተረ ግ አስጌጠ፡ አስዋበ፡ አሳመረ።

ኮነተሸ ግ በጣም አሳጠሮ ቆረጠ።

ኩንትሽ ቅ በጣም አጭር።

ኩንትሽ አለ ግ ተኮነተሸ።

ኩንትሽ አደረገ ግ ኮነተሸ።

ተኮነተሸ ግ በጣም አጠረ።

ኮነነ ግ 1.ቀጣ (ነፍስን)። 2.ወነጀለ፤ ጥፋተኛ አድርጎ አቀረበ።

ኩነኔ ስ የነፍስ ቅጣት (ከሞት በኋላ በገሃነም ይደርሳል ተብሎ የሚታመንበት)።

ኩነኔ ገባ የሚያስኮንን ስራ ሰራ።

ኮናኝ ቅ የሚኮንን፡ ፍርድ የሚሰጥ።

አስኮናኝ ቅ 1.የሚያስኮንን። 2.አቅመ ቢስ፤ ደካማ፤ ምስኪን (ለኩነኔ ምክንያት የሚሆን)።

***ኮናተረ**

ኮንትራት ስ 1.የቁርጥ ስራ ውል ወይም ስምምነት። 2.ለተወሰነ ጊዜ የተወሰነ ግልጋሎት ለመስጠት ወይም ለማግኘት የሚያስችል ውል ወይም ስምምነት።

ኮንትራት ወሰደ የስራ ወይም የሌላ ኮንትራት ውል ተዋዋለ፤ ተቀበለ ።

የኮንትራት ሰራተኛ ስ ለተወሰነ ጊዜ እንዲያገለግል የተቀጠረ ሰራተኛ።

ተኮናተረ ግ 1.የቁርጥ ስራ ለመስራት ወይም ለማሰራት ተዋዋለ ወይም ተስማማ። 2.ለተወሰነ ጊዜ የተወሰነ ግልጋሎት ለመስጠት ወይም ለማግኘት ተዋዋለ ወይም ተስማማ። 3.ገንዘብ እየተከፈለበት አገልግሎት እንዲሰጥ ተደረገ (መኪና፥ ቤት፥...)።

ተኮናታሪ ቅ የስራ ተቋራጭ፤ የተወሰነ ስራ በተወሰነ ክፍያ የሚሰራ። 2.በተወሰነ ክፍያ የተወሰነ ግልጋሎት (የቤት፥ የመኪና፥...) ለማግኘት ከባለ ሃብቱ ጋር የተዋዋለ።

አኮናተረ ግ የተወሰነ ክፍያ ለማግኘት አንድን ነገር (ለምሳሌ ቤትን) ለተወሰነ ጊዜ ለተገልጋይ (ለተኮናታሪ) ሰጠ።

አኮናታሪ ቅ አንድን ስራ ወይም መገልገያ (ለምሳሌ ቤትን) ለተኮናታሪ የሰጠ ወይም የሚሰጥ (ሰው)።

ኮናኝ "ኮነነ" ስር ተመ.

ኮንበር "ኮምበር"ን ተመ.

ኮንትራክተር ስ የስራ ተቋራጭ።

ኮንትሮል ስ ተቆጣጣሪ።

ኮንትሮባንድ ስ ለመንግስት ቀረጥ ሳይከፈልበት በድብቅ የሚካሄድ ህገ ወጥ ንግድ።

ኮንዶም ስ ያልተፈለገ እርግዝናንና ልዩ ልዩ የአባለዘር በሽታዎችን ለመከላከል ሲባል ወሲብ በሚደረግበት ወቅት በወንዱ አባለዘር ላይ የሚጠለቅ ከላስቲክ መሰል ነገር የሚሰራ መከላከያ።

ኮንግረስ ስ ጉባኤ።

ኮንጎ [ጫማ] ስ የላስቲክ ጫማ።

ኮከብ (ብ.ቁ.**ከዋክብት**) ስ 1.በምሽት በሰማይ ላይ ብልጭ ብልጭ እያሉ ከሚታዩና ብርሃን ካላቸው አካላት አንዱ። 2.የአንድን ሰው ባህርይ ይወክላል፥ የወደፊት እድሉንም ይወስናል ተብሎ የሚታመንበት የኮከቡ ስምና ባህርይ። 3.በኮከብ ቅርፅ የተሰራ የወታደራዊ ማእረግ ምልክት። 4.እውቅ፥ ተደናቂ፥ ጎበዝ። *ኮከብ ተዋናይ*።

ኮከባቸው ገጠመ ተስማሙ፥ ተኳኋኑ።

ኮከብ ቆጠረ ሰዎች በሚወለዱበት ቀንና ሲወለዱ በሚኖሩት ከዋክብት መካከል ያለውን ግንኙነት ወይም የሰዎችን ስምና የእናቶቻቸውን የመጠሪያ ስም ፊደሎች ቀጥር ከልዩ ልዩ ከዋክብት ጋር በማገናዘብ ስለሰዎቹ ባህርይና የወደፊት እድል በቅድሚያ ተናገረ፥ ጠነቆለ፤ መፅሃፍ ገለጠ።

ኮከብ ቆጠራ ስ ኮከብን በመቁጠር ስለሰዎችና ስለተለያዩ ሁኔታዎች የሚደረግ ትንበያ(ለትንበያው የሚገለገሉባቸው ከዋክብቶች አቅራብ፥ቀውስ፥ ጀደይ፥ ደለው፥ ሁት፥ ሃመል፥ ተውር፥ጀውዛ፥ሸርጣን፥ አሰድ፥ ሰንቡላ የተባሉት ናቸው)።

ኮከብ ቆጣሪ ስ ኮከብ በመቁጠር የሚጠነቁል፤ መፅሃፍ ገላጭ።

ኮከብ ጫነ የኮከብ ምልክት ያለው ወታደራዊ ሹመት አገኘ።

ኮከበ ነጣሳ ቅ እድለ ቢስ።

ኮኮን (ኮኮኔ) ስ 1.የአውራ ዶሮ ቁንጮ። 2.ኩኩሉ ማለት የጀመረ ዶሮ።

ኮክ ስ ሞለል ያለ ክብ ቅርፅ ያለው፥ የቆዳው ቀለም አረንጓዴ መሰል ቢጫ ሆኖ በሚበላውና በለስላሳው ክፍል ውስጥ የተሸፈነ ጠንካራና ሻካራ ፍሬ በውስጡ የሚገኝ የፍራፍሬ አይነት፤ ፍሬውን የሚያፈራው ተክልም ኮክ ይባላል።

ኮክቴል ስ መጠጥና ቀላል ምግብ የሚገኝበትና ሰዎች ቆመው የሚጋበዙበት የግብዣ አይነት።

ኮኮ "እንኮኮ"ን ተመ.

ኮኮኔ "ኮኮን"ን ተመ.

ኮየሰ ግ 1.ኩይሳ ሰራ። 2.ቆለለ፥ ከመረ (አፈርን)።

ኩይሳ ስ አፈር በመቆለል ምስጦች ለራሳቸው የሚሰሩት መኖሪያ ቤት።

ኮደኮደ ግ እግር ተወርች አሰረ።

ኮደደ "ሆደደ^{2}"ን ተመ.

ኮዳ ስ ከፕላስቲክ ወይም ከኒኬል፥... የሚሰራና ማንገቻ ያለው የመንገደኞች ውሃ መያዣ።

ኮድ ስ 1.ምስጢራዊ የሆነ መልእክትን ለማስተላለፍ ወይም ረዥም መልእክትን አሳጥሮ ለማቅረብ የሚያገለግል ቋንቋ ወይም ምልክት። 2. መለያ፥ ልዩ ምልክት(ለአንድ ነገር፥ እቃ፥... የተሰጠ ወይም የሚሰጥ)።

ኮፈሰ ግ 1.በሚዶ ነቀሰ ወይም አበጠረ (ፀጉርን)። 2.በከንቱ ውዳሴ ካበ፥ አሞገሰ፥ አኩራራ።

ኩፍስ ቅ 1.በደንብ ተስተካክሎ የተበጠረ ጎፈሬ። 2.ጥሩ ልብስ በመልበስ የተሸሞነሞነ ወይም የተዋበ። 3.ጀንን።

ተኮፈሰ ግ 1.ጥሩ ልብስ በመልበስ ተሸሞነሞነ፥ ተዋበ። 2.ተጀነነ። 3.አኮረፈ።

ኮፈተረ ግ በአንድነት ጠቀለለ፥ ጠመዘዘ (ሰበዝን)።

***ኮፈነነ**

ኮፍናና ቅ ጀንን።

ተኮፋነነ ግ ተኩራራ፥ ታጀረ፥ ተዘባነነ።

ኮፈን ስ የመኪናውን ሞተር ከዝናብና ከአቧራ የሚከላከል የሞተር ክዳን።

***ኮፈኮፈ**

ኮፈኮፍ (ኮፍኳፋ) ቅ 1.ልክክ የማይል፡ የሚንከረፈፍ (ልብስ)። 2.(ስድብ) ቀጡ።

ኩፍኩፍ አለ ግ ተንኮፈኮፈ።

ተንኮፈኮፈ ግ 1.ጎረበ፡ ቆረበበ፡ ተነሳ፡ ሲሳፕ ቀረበ (የሰውነት ቆዳ፡...)። 2.አኮረፈ።

አኮፈኮፈ ግ ጎረበ፡ ቆረበበ፥ ተነሳ፡ ሲሳፕ ቀረበ (የሰውነት ቆዳ፡...)።

ኮፈፈ

ኩፍታ^{1} ስ 1.ኩፍ ማለት (ሊጥ)። 2.ኩርፍታ።

ኩፍታ^{2} ስ ሊጡ ኩፍ ካለ በኋላ የተጋገረ ቂጣ (ብዙውን ጊዜ የሽምብራ)።

ኮፈፍተኛ (ኮፈፍታ) ስ አፍለኛ፡ በጣም ሳይቦካ የተጋገረ እንጀራ ወይም ቂጣ።

ኩፍ (ኩፍፍ) አለ ግ 1.ተነሳ፡ ብድግ አለ፡ ቦካ (ሊጥ)። 2.አኮረፈ።

ኮፈፍ አለ ግ ልስቅ ወይም ልጥፍ ሳይል ቀረ፡ ወደላይ ጉብ ብሎ ታየ።

ኮፍናና "***ኮፈነነ**" ስር ተመ.

ኮፍኳፋ "***ኮፈኮፈ**" ስር "**ኮፈኮፍ**"ን ተመ.

ኮፒ ስ ቅጂ፡ ግልባጭ (የስእል፥ የፅሁፍ፡...)።

ኳ^{1} የ"**ከ**" ፊደል ፍንፅቅ ዘር።

ኳ^{2}

ኳ አለ ግ እንደ እንጨት፥ ድንጋይ፡ ሳህን፡... ያለ ነገር ሲወድቅ ወይም ሲጋጭ የሚሰጠውን አይነት ድምፅ ሰጠ።

ኳ አደረገ ግ እንደ እንጨት፡ ድንጋይ፥ ሳህን፥... ያለ ነገር ሲወድቅ ወይም ሲጋጭ የሚሰጠውን አይነት ድምፅ እንዲሰጥ አደረገ፤ ኳ አደረገ።

ኳኳታ (ኳኳቴ) ስ ድግግሞሽ ያለው የሚንኳኳ ድምፅ።

ኳ ኳ አለ ግ ተንኳኳ።

ኳ ኳ አደረገ ግ አንኳኳ።

ተንኳኳ ግ 1.ኳ የሚል ድምፅ በተደጋጋሚ ሰጠ። 2.ተመታ፡ ተቆረቆረ (በር፥...)።

አንኳኳ ግ 1.በተደጋጋሚ ኳ የሚል ድምፅ እንዲሰጥ አደረገ። 2.ቆረቆረ፡ መታ (በርን፡...)።

ኳ^{3}

ኳ አለ ግ በጣም ደረቀ።

ኳ አደረገ ግ በጣም አደረቀ።

ኳ^{4}

ኳ አለ ግ ወለል ወይም ፍንትው አለ፡ ጠራ። *ሰማዩ ኳ ብሎ ጠርቷል።*

ኳለ ግ 1.የአይንን ቅንድብ በኩል ቀባ፥ አስጌጠ። 2.ቀባ፡ ፃፈ (በቀለም)።

ኩል ስ በዱቄት ወይም በእርሳስ መልክ ተዘጋጅቶ ሴቶች የአይናቸውን ቅንድብ በመኳል የሚያስጌጡበት ጥቁር የማእድን አይነት።

ተኳለ ግ የአይን ቅንድብ በኩል ተጌጠ።

የተኳለ የተዳረ በስርአት ተድሮ ለወግ ለማእረግ የበቃ (ልጅ)።

ተኳኳለ ግ ተጊያጊያጠ፥ ተሽሞነሞነ።

***ኳስ**

ኳስ ስ ለልዩ ልዩ የጨዋታ አይነቶች እንዲያገለግል በተለያየ መጠን ከጨርቅ ወይም ከቆዳ ወይም ከላስቲክ ወይም ከሌላ ነገር የሚሰራ ድብልብል ቅርፅ ያለውና ውስጡ ባዶ ወይም ድፍን የሆነ መጫወቻ። *የእጅ ኳስ/ የጠረጴዛ ኳስ።*

ኳስ አበደች ኳስ ወደሰማይ ጎነች።

ኳስ ሜዳ ስ ኳስ ጨዋታ የሚደረግበት ቦታ ወይም ሜዳ(ብዙውን ጊዜ የእግር ኳስ) ።

ተኳሰ ግ እንደ ኳስ ሆነ፡ ተድበለበለ።

አኳሰ ግ 1.እንደ ኳስ አደረገ፥ አድበለበለ። 2.ኳስ አነጠረ።

ኳሸ^{1} ግ 1.ያልሆነውን እንደሆነ አድርጎ በሽንገላ አወደሰ፡ ካበ፡ አሞካሸ። 2.ዋሸ፡ ጉራ ነዛ። 3.አጋነነ፤ ትንሺን እውነት በትልቅ ውሸት አጎልምሶና አጋኖ ተናገረ። 4.ያመሰገነ መስሎ ተሳደበ፥ ተረበ።

ኩሸት ስ 1.ጉራ። 2.ውሸት። 3.ትንሺን እውነት በትልቅ ውሸት አጎልምሶና አጋኖ ለመናገር የሚያስችል የቅኔ መንገድ።

ኩሸተኛ ቅ 1.ያመሰገነ መስሎ የሚሳደብ፥ ተራቢ። 2.ዋሾ። 3.ጉረኛ። 4.ያልሆነውን እንደሆነ አድርጎ በሽንገላ የሚያወድስ፡ የሚካብ፥ የሚያሞካሽ።

አኳሸ ግ 1.ያልሆነውን እንደሆነ አድርጎ በሽንገላ አወደሰ፥ ካበ፡ አሞካሸ። 2.ደለለ፥ አሞኘ፡ እንዲጎመጅ ወይም እንዲጓጓ አደረገ (በውሸት)።

ኳሸ^{2} ግ ረበሸ፡ አስቸገረ (ህፃን)።

ኳተ ግ ቆፈረ፥ ማሰ፥ ፋረ።

ኳተነ ግ ማሰነ፡ ደከመ፥ ለፋ (በእግር በመሄድ)።

ኳንክ ስ 1.ኮከኔ። 2.በአውራ ዶሮ አንገት ላይ የሚገኝና ኮከኔ የሚመስል እንጥልጥል።

ኳንኳ ስ ታንኳ።

ኳክ

ኳክ አለ ግ ጮሀ፥ ድምፅ አሰማ (ዶሮ)።

ኳድሮ ስ የመኪናን ሞተር ለማስነሳት የሚረዳ የመኪና እቃ።

ወ

ወ ከ"ኸ" ፊደል ዘር ቀጥሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል (ግእዙ ሆሄ)።

ወህኒ [ቤት] ስ እስር ቤት፣ ከርቸሌ።

ወህኒ ወረደ ታሰረ ወይም እስር ቤት ገባ።

ወለላ ቅ ከዳ ወይም ሰፌፍ፣... የሌለበት ንፁህ (ማር) ።

ወለሌ "ወለል¹" ስር ተመ.

ወለል ስ 1. በአፈር የተደለደለ ወይም በጣውላ ወይም በሲሚንቶ፣...የተሸፈነ የቤት ውስጥ የመሬት ገፅታ። *ወንበር የለም፣ ወለሉ ላይ ተቀመጥ ።* 2.ውሃ ልክ የተስተካከለ፣ ተጋደለ ያልሆነ።

ወለል¹

ወለሌ ስ የስቃይ ወይም የሃዘን ዋይታ፣ ጩሀት ።

ወለል ያድርገኝ እኔ ልዘን ወይም ልንከራተት ለሚሃለትና ሃዘንን ለመግለፅ የሚነገር አባባል ።

ወለል²

ወለል አለ ግ 1. ብርሃን ሆነ፣ ግልፅ አለ። 2. ጠራ፣ ፀዳ። 3. በሰፊው ተከፈተ (በር)።

ወለል አደረገ ግ 1. ግልፅ አደረገ፣ አጠራ፣ አፀዳ ። 2. በሰፊው ከፈተ (በርን)።

***ወለመ**

ወለምታ ስ ከትክክለኛ ቦታው በመዛወሩ ወይም በመዛነፉ፣ እጥፍ በማለቱ፣... የሚሰማ የስር ላይ ወይም የአጥንት መጋጠሚያ ህመም ።

ወለም አለ ግ ከትክክለኛ ቦታው በመዛወሩ ወይም በመዛነፉ ህመም ተሰማ (የአጥንት፣ የስር)።

ወለም ዘለም አለ ግ ስራ ፈትቶ ወዲያ ወዲህ አለ፣ አውደለደለ፣ አደሸደሸ ።

***ወለመመ**

ወልማማ ቅ (ስድብ) ወልጋዳ፣ ጠማማ፣ ሸፋፋ ።

ተወላመመ ግ ተዛወረ፣ ተዛነፈ፣ ተጣመመ፣ ተወላገደ ።

አወላመመ ግ አዛወረ፣ አዛነፈ፣ አጣመመ፣ አወላገደ ።

***ወለመጠ**

ወልማጣ ቅ (ስድብ) 1. ለማጣ፣ ቀጥተኛ የሆነ አካላዊ አቋም የሌለው። 2. ጠንከር ብሎ መስራት የማይወድ፣ አልምጥ፣ ዋልጌ። 3. የተናገረውን ቃል የማያከብር፣ ወላዋይ ።

ውልምጥምጥ ቅ ልምጥምጥ፣ አቋሙ ወይም አካላዊ አፈጣጠሩ ቀጥተኛ ያልሆነ ።

ተወላመጠ ግ ስራ ፈትቶ ወዲያ ወዲህ አለ፣ ተዘዋወረ ።

ወለምታ "*ወለመ" ስር ተመ.

ወለሰ ግ ሳያቋርጥ ቀስ እያለ ለብዙ ሰአት ዘነመ ።

ወሊስ ስ ሳያቋርጥ ቀስ እያለ ለብዙ ሰአት የሚጥል ዝናብ ።

ወለሸ ስ ውሃ የተኛበት ለም መሬት ።

ወለቀ ግ 1. ተነቀለ። *ጥርሱ ወለቀ።* 2. ወጣ፣ ተነሳ፣ ተገፈፈ። *ልብሱ ወለቀ።* 3. ተዛባ፣ ተዛነፈ፣ ቦታውን ለቀቀ። *ክንዱ ወለቀ።*

ወላቃ ቅ 1. ሙሉ ያልሆነ፣ የወለቀለት። 2. ጥርሱ የተነቀለ፣ ጥርሰ ወላቃ እየተባለም ይጠራል።

ውልቃት ስ የአጥንት መጋጠሚያ ከቦታው መዛባት።

ውልቅ አለ ግ 1. ሹልክ ብሎ ወጣ ወይም ሄደ። 2. ሙልጭ ብሎ ወጣ፣ ለቀቀ (እድፍ)።

ወላለቀ ግ 1. ተንቃቀለ፣ ተለያየ፣ ተበታተነ፣ ተፈታታ። 2. ደከመ፣ ዛለ፣ ባመነ። *ብዙ ከመሄድ የተነሳ ሰውነቷ ወላለቀ።*

ውልቅልቅ ቅ የወላለቀ፣ የፈራረሰ፣ የተንቃቀለ።

ውልቅልቁ ወጣ 1. ተንቃቀለ፣ ተበታተነ፣ ተፈታታ። 2. በጣም ደከመ፣ ዛለ።

አወለቀ ግ 1. አነሳ፣ አወጣ፣ ገፈፈ (ልብሱን፣ ጫማውን፣ ...ከላዩ ላይ)። 2. ነቀለ፣ አወጣ። 3. (ዘይ.) መታ፣ ደበደበ። *በቦክስ አወለቀው ።*

አወላለቀ ግ 1. አወለቀ (ልብሱን፣ ጫማን፣...)። 2. በታተነ፣ ፈታታ፣ ለያየ ። *የመኪናውን ብሎኖች አወላለቀ ።*

አውለቀለቀ ግ አደከመ፣ አዛለ (ሰውነትን)።

***ወለበ**

ወላባ ቅ ቀትረ ቀሊል፣ ነሁላ፣ ሾላካ፣ ጥላቢስ።

ውልብ አለ ግ ታይቶ ጠፋ፣ ከመቅፅበት ሽው ብሎ አለፈ ።

ወለብላባ ቅ ለፍላፊ፣ ምላሰኛ ።

ውልብልብ ቅ የሚውለበለብ፣ የሚርገበገብ።

ውልብልቢት ስ 1. የኮባ፣ የዘንባባ፣ የተምር ዛፍ ቀንበጥ ወይም ጫፍ ። 2. የእሳት ላንቃ። 3.

ከብደት በሚዛን ላይ ሲወጣ መጠኑን እስከምትጠቁም ድረስ ወዲያ ወዲህ የምትዋዥቅ ምልክት፡ የሚዛን ምላስ ፡፡ 4. ብዙውን ጊዜ በንፋስ የሚውለበለብ፡ የሚሽከረከር ማንኛውም ነገር (ለምሳሌ የአውሮፕላን ውልብልቢት)፡፡

ተውለበለበ ግ 1. ተወዛወዘ፡ ተንቃነቀ፡ ተርገበገበ (ለምሳሌ ባንዲራ)፡፡ 2. ለፈለፈ ፡፡

አውለበለበ ግ ወዘወዘ፡ ነቀነቀ፡ አርገበገበ፡፡

ወለባ ስ በድሮ ጊዜ ፀጉር ላይ የሚሰካና ከብር ወይም ከወርቅ... የሚሰራ የጌጥ አይነት፡፡

ወለብላባ "*ወለበ" ስር ተመ.

ወለከፈ ግ አደናቀፈ፡ ሰነከለ ፡፡

ወልካፋ ቅ (ስድብ) ደንቃፋ፡ ሰንካላ፡ ሽፋፋ፡ አካሄድ የማይችል ፡፡

ውልክፍክፍ ቅ ደንቅፍቅፍ፡ ስንክልክል፡ ሽፋፋ፡፡

ተወለካከፈ ግ ተደነቃቀፈ፡ ተሰነካከለ ፡፡

ተወላከፈ ግ 1. ተደናቀፈ፡ ተሰናከለ፡፡ 2. ተንሻፈፈ፡ ተጣመመ፡፡

አወለካከፈ ግ አደነቃቀፈ፡ አሰናከለ፡፡

አወላከፈ ግ 1. አደናቀፈ፡ አሰናከለ፡፡ 2. አንሻፈፈ፡ አጣመመ ፡፡

ወለወለ ግ 1. ጠረገ፡ አሰሰ፡ አበሰ፡ አፀዳ፡ አጠራ ፡፡ 2. ደጋግሞ በጥፊ መታ፡፡ *ልጁን በጥፊ ወለወለው፡፡*

መወልወያ ስ ማበሻ፡ መጠራረጊያ፡ ማሰሻ፡ ማፅጃ (ጨርቅ ወይም ሌላ ነገር)፡፡

ውልውል ቅ የተጠረገ፡ የፀዳ፡ የተወለወለ፡፡

ተወለወለ ግ ተጠረገ፡ ታሰሰ፡ ታበሰ፡ ፀዳ፡፡

አወለወለ ግ ፊቱ አማረበት ወይም ወዛ ፡፡

ወለወልዳ ቅ አሳባቂ፡ ወሽካታ ፡፡

ወለደ ግ 1. ልጅ አገኘ፡ ዘር ተካ፡ ረባ፡፡ 2. በዛ፡ ተባዛ፡ በረከተ፡... ፡፡ 3. አተረፈ፡ አራጣ አስገኘ (ገንዘብ፡)፡፡ 4. እንደራሱ ልጅ አደረገ (ክርስትና በማንሳት፡ ጡት በማጥባት፡...)፡፡ 5. እንደማሽላ፡ ገብስ፡... ያሉ እህሎች ከአደበደቡ በኋላ ፍሬ የሚይዘው ክፍላቸው ወጣ፡ ዘረዘረ፡፡ 6. አዳነ፡ አወጣ፡ አተረፈ (ከችግር)፡፡

ወለደች ተገላገለች ፡ ልጅ አገኘች (እርጉዝ የነበረች እንስት)፡፡

ውለዱ ክበዱ (ምር.) ልጅ አግኙ፡ ክበሩ፡፡

ውለድ(ውለዱት) ከየትም ብለህ አምጣ (አምጡት)፡፡

ወለድ ስ የገንዘብ ትርፍ፡ አራጣ (በማበደር የሚገኝ ወይም በመበደር የሚከፈል) ፡፡

ወለድ አግድ ስ አበዳሪዎች በገንዘብ ትርፍ ወይም አራጣ ፋንታ የተበደሩን ቤት፡ መሬት፡... በመያዝ የሚጠቀሙበት የብድር ውል አይነት ፡፡

ወሊድ ስ በመውለድ ላይ መሆን፡ *በወሊድ ሞተች ፡፡*

ወላዲተ አምላክ ስ ማርያም፡ የክርስቶስ እናት፡፡

ወላድ ቅ 1. የወለደች፡ የምትወልድ፡ መካን ያልሆነች፡፡ 2. ብዙ የምትወልድ ወይም የወለደች፡፡ ስ 3. እናት፡፡ *ወላድ በድባብ ትሂድ፡፡*

ወላጅ ስ እናት ወይም አባት፡፡ *ወላጅ አባቱ ሌላ ነው፤ ይህኛው አሳዳጊ ነው፡፡*

ውላጅ ቅ ከቤት አገልጋዮች የተወለደ (ልጅ)፡፡

ውልድ ቃል ስ በቋንቋ የቃላት አመሰራረት ህግ መሰረት ቀደም ሲል በነበረ ቃል ላይ ተመስርቶ የሚፈጠር ወይም የተፈጠረ ሌላ ቃል፡፡

ልደታ በፊደል ተራው ተመ.

ልደት በፊደል ተራው ተመ.

ልጅ በፊደል ተራው ተመ.

ተወለደ ግ 1. ልጁ ከማህፀን ወጣ፡፡ 2. ከተወሰነ ዘር፡ ሰው፡ ቤት፡... ተገኘ፡፡ 3. መጣ፡ ተገኘ፡ ታየ፡፡ *አዲስ ነገር ተወለደ፡፡*

እንደገና ተወለደ ደርሶበት ከነበረው ከፍተኛ ችግር፡ ስቃይ ዳነ ወይም አመለጠ፡፡

ተወላጅ ቅ ወገን፡ ዘር፡ ቤተሰብ፡ ዘመድ፡፡

ትውልድ ስ 1. በአንድ ዘመን፡ ወቅት ያለ ህዝብ፡፡ 2. የተወለዱበት ቦታ ወይም ዘር ፡፡

ተዋለደ ግ 1. ተራባ፡ ተባዛ፡፡ 2. የአንዱ ወገን የሌላውን ወገን አግብቶ በመውለድ ተዛመደ፡፡

አዋለደ ግ 1. ወላድን በወሊድ ጊዜ ረዳ፡ አገዘ፡፡ 2. አንዱ ከሌላው እንዲወልድ አደረገ፡ አራባ፡ አባዛ፡፡

ማዋለጃ ክፍል ስ ሴቶች ምጥ በያዛቸው ጊዜ በሃኪም እየታገዙ የሚወልዱበት ክፍል ፡፡

አዋላጅ ቅ የሚያዋልድ፡ ወላድን በምጥ ጊዜ እንድትወልድ የሚረዳ (ሃኪም፡ ባለሙያ) ፡፡

ወለድ^1 **"ወለደ"** ስር ተመ

ወለድ^2 ስ ከካርታ መጫወቻዎች አንዱ፡ ከአስር ቁጥር ካርታ ቀጥሎ የሚገኝ ወይም የሚከተል ካርታ፡፡

ወለገመ ግ ጠመመ፡ ወለገደ፡፡

ወልጋማ ቅ ጠማማ፡ ወልጋዳ፡፡

ውልግምት ቅ ክፉ፡ ጠማማ፡ ቅንነት የሌለው፡፡

ተወላገመ ግ ተጣመመ፡ ተወላገደ፡፡

አወላገመ ጎ አጣመመ፡ አወላገደ።

ወለገደ ጎ ጠመመ፥ ጎበጠ።

ወልጋዳ ቅ ጠማማ፡ ጎባጣ፡ ጠመዝማዛ የሆነ (እንጨት፡ እግር፡...)።

ውልግድ ቅ የጎበጠ፡ ጎባጣ።

ውልግድግድ ቅ ጉብጥብጥ ያለ፡ ከብዙ ቦታ ላይ የተጣመመ።

ተወለጋገደ ጎ ብዙ ቦታ ላይ ተወላገደ፡ በጣም ጥምም፡ ጥምዝዝ አለ።

ተወላገደ ጎ ጠማማ ሆነ፥ ተጠማዘዘ።

አወለጋገደ ጎ ብዙ ቦታ ላይ አወላገደ።

አወላገደ ጎ አጣመመ፡ ጎባጣ፡ ጠምዛዛ አደረገ።

ወለፈሰ ጎ የማይረባ፡ ልፍስፍስ፥ ቁም ነገር የሌለው ሆነ።

ወልፋሳ ቅ (ስድብ) የማይረባ፡ ልፍስፍስ፡ ልክስክስ፥ በቁም ነገር ስራ የማይጠመድ።

ውልፍስፍስ ዝ.ከ.

ወለፈተ ጎ 1. ያልተጠየቀውን ቀባጠረ፡ ዘባበደ፡ በአነጋገሩ ቁም ነገር የሌለው ሆነ። 2. ስራ ፈቶ ወዲያ ወዲህ አለ፡ ቦዘኔ ሆነ።

ወልፋታ ቅ (ስድብ) 1. ወልፋሳ፡ ቀባጣሪ። 2. ስራ ፈት፡ ዟሪ ።

ወለፈንድ ቅ አመለ ጠማማ፡ ወልጋዳ።

የወለፈንድ(የወለፈንዳ) ከሰው የማይስማማ፡ የማይገጥም (ስራ)። *ስራዋ ሁሉ የወለፈንድ ነው።*

ወሊስ "**ወለሰ**" ስር ተመ.

ወሊድ "**ወለደ**" ስር ተመ.

ወላ

ወላ ሸማላ አለ ጎ ወላወለ፡ የሚያደርገውን አያውቅም አለ ፡

ወላለቀ "**ወለቀ**" ስር ተመ.

ወላሳ ቅ አዛኝ፡ ርህሩህ፡ ደግ፡ ገር ።

ወላቃ "**ወለቀ**" ስር ተመ.

ወላባ "**ወለበ**" ስር ተመ.

ወላንሳ ስ 1. ቀይ ከፋይ ወይም አረንጓዴ ባለወርቅ ዘርፍ ሆኖ በሁፋንና በመከዳ ላይ የሚዘረጋ፡ የሚነጠፍ ለስላሳ ምንጣፍ። ቅ 2. በውን የማያስቀይም አመለ ለስላሳ፡ ጥሩ።

ወላወለ ጎ 1. ተነቃነቀ፡ ተወዛወዘ፡ አልረጋ አለ። 2. አመነታ፡ ሁለት ሃሳብ ሆነ፡ አልቆርጥ አለ።

ወላዋይ ቅ ሁለት ልብ፥ ተጠራጣሪ፡ የሚያመነታ፡ ቆራጥነት የሌለው ።

አወላወለ ጎ አመነታ፥ ተጠራጠረ ።

አወላዋይ ቅ 1. አጠራጣሪ። 2. የሚያመነታ፡ ወላዋይ ።

*ወላዳ

ተወላዳ ጎ 1. ደፈረ፡ ተሰናዘረ (የጀግንነት ወይም ሌላ ስራ ለመስራት)። 2. ተዝናና፥ ተቀናጣ።

አወላዳ ጎ 1. አሰናዘረ፡ ወዲያ ወዲህ ማለት አስቻለ። 2. አዝናና፡ አቀናጣ ።

ወላድ "**ወለደ**" ስር ተመ.

ወላጅ ዝ.ከ.

ወላፈን ስ ከሩቅ የሚጋረፍ የእሳት ነበልባል ወይም ሳንቃ ።

ወላፎ ቅ ሸፋፋ ።

ወል

በወል መዋ. በጋራ። *መሳሪያውን በወል መጠቀም እንችላለን ።*

የወል ቅ የጋራ ።

የወል ስም ስ ተመሳሳይ ነገሮች በአንድነት ወይም በጋራ የሚጠሩበት የስም አይነት ።

ወልማማ "**ወለመመ**" ስር ተመ.

ወልማጣ "*ወለመጠ" ስር ተመ.

ወልካሳ(ውልክስ) ቅ አንካሳ፡ ተልካሻ፡ የማይረባ ።

ወልካፋ "**ወለከፈ**" ስር ተመ.

ወልይ ስ ስለወደፊት ሁኔታዎች ይተነብያል የሚባል ሰው፡ ጠንቋይ ።

ወልድ ስ (ክር.) ቅድመ አለም ከአብ ያለ እናት፡ ድህረ አለም ከቅድስት ድንግል ማርያም ያለ አባት የተወለደ የአብ የባህርይ ልጅ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ።

ወልጋማ "**ወለገመ**" ስር ተመ.

ወልጋዳ "**ወለገደ**" ስር ተመ.

ወልጌ "**ዋልጌ**" ን ተመ.

ወልፋሳ "**ወለፈሰ**" ስር ተመ.

ወልፋታ "**ወለፈተ**" ስር ተመ.

ወልፍ ስ ሱስ (የቡና፡የሲጋራ፡...)።

ወመቴ ስ ስራፈት፡ ዱርዬ፥ ወሮበላ።

ወመኔ ስ ዱርዬ፥ ወሮበላ ።

ወማይ ስ ቀለሙ ጠቆር ያለ አረንጓዴ ሃር የሚመስል ወፍ።

ወረሃ ቅ እግሮቹ እንደደጋን የጎበጡ።

ወረረ ጎ 1. የሌሎችን ሃገር በወታደራዊ ሃይል ያዘ ወይም በቁጥጥር ስር አደረገ ። 2. አንድን አካባቢ በብዛት አለበሰ፡ ሸፈነ (ለምሳሌ አንበጣ፡ ጉንዳን)። 3. በሰውነት ወይም በገላ ላይ

የመዘሚያን፡ የመሰቅጠጥ ስሜት ተሰማ። 4. ዘረፈ፥ በዘበዘ፡ በረበረ።

ወረር አደረገ ግ በመጠኑ ሳሞቀ፡ ሞቅ አደረገ። *ልብሱ ይሰጣና በሃይ ወረር ያድርገው ።*

ወሮበላ ስ ዘራፊ፡ ዱርዬ፡ ዘርፎ ወይም ቀምቶ የሚበላ።

ወረራ ስ 1. ዝበዛ፡ ዘረፋ። 2. የሌሎችን አገር ለመያዝ የሚደረግ ጦርነት ወይም ዘመቻ ።

ወረርሽኝ ስ ከአንዱ ወደ ሌላው እየተላለፈ በአንድ ጊዜ ብዙ ሰዎችን የሚያጠቃ እንደ ጉንፋን፡ ተስቦ፡... ያለ በሽታ ።

ወራሪ ስ አገርን በጦር ሃይል በቁጥጥር ስር ለማድረግ የሚወር ሰራዊት፡ ዘራፊ ።

ተወረረ ግ 1. ተያዘ፡ በቁጥጥር ስር ዋለ (አንድ ሃገር በሌላ ሃገር ጦር)። 2. ተሸፈነ፡ ሰበበ (አንድ ነገር፡ አካባቢ)። 3. ተዘረፈ፡ ተበዘበዘ፡ ተበረበረ ።

የተወረረ ይመስላል ጭር ብሏል (አካባቢ)።

ወረር ስ የፊት አወራረድ፡ ገፅታ፡ መልክ።

ወረርሽኝ "ወረረ" ስር ተመ.

ወረሰ ግ 1. ከወላጁ፡ ከዘመዱ በኑዛዜ የተሰጠውን ንብረት ወሰደ፡ ተቀበለ፡ የንብረቱ ባለቤት ሆነ። 2. የሌላውን ሰው ንብረት በቁጥጥር ስር አደረገ፡ ወሰደ (ያለካሳ፡ ያለክፍያ፡ ያለፈቃድ)። 3. ተቀበለ፡ ተማረ። *ወጣቱ የአባቶቹን እውቀት ወርሷል*። 4. ያዘ፡ አለበሰ፡ አጠለቀ፡ ዋጠ (ለምሳሌ እከክ ሰውነትን፡ አረም መሬትን፡...)።

ወራሽ ስ የሚተላለፍለትን ሃብት፡ ትምህርት፡... በባለቤትነት የሚቀበል፡ ተረካቢ ።

ውርስ ቅ የተወረሰ፡ በመውረስ የተገኘ (ንብረት፡ እውቀት፡ ባህል፡...)።

ውርስ አደረገ ግ ወረሰ፡ በእጅ አገባ፡ ያዘ (የሌላ ሰውን ንብረት)።

ውርስ አደረገ ግ አለበሰ፡ አጠለቀ፡ ያዘ፡ ክብብ አደረገ (ለምሳሌ እከክ ሰውነትን፡ አረም መሬትን፡...)።

ተወረሰ ግ 1. ያለካሳ፡ ያለክፍያ ተወሰደ ወይም ተወሰደበት (ሃብቱ፡ ንብረቱ፡...)። 2. ለተከታይ ተላለፈ፡ ተሸጋገረ። 3. በብዛት ተያዘ፡ ተከበበ፡ ተወረረ (በእከክ፡ በአረም፡ በቅማል፡...)።

ተወራረሰ ግ 1. በአንድ ወረቀት ላይ ያለ መረጃ በሌላ መዝገብ ላይ ሰፈረ፡ ተመዘገበ። 2. ተመሳሰለ፡ አንድ አይነት ባህርይ ያዘ ።

ተወራራሽ ቅ አንዱ በሌላው ቦታ ሊተካ የሚችል፡ ተመሳሳይነት ወይም ተቀራራቢነት ያለው።

አወረሰ ግ ሰጠ፡ አስተላለፈ፡ አሸጋገረ (ሃብትን፡ እውቀትን፡...)።

አወራረሰ ግ በአንድ ወረቀት ላይ የሰፈረን መረጃ በሌላ መዝገብ ላይ አሰፈረ፡ መዘገበ ።

ወረቀት ስ 1. ከእንጨት፡ ከልጥ፡ ከገለባ፡ ከጨርቃ ጨርቅና ከመሳሰሉ ነገሮች በስሱ እየተሰራ ለፅሕፈትና ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል እቃ፡ የፅሕፈት መሳሪያ። 2. ደብዳቤ፡ ማዘዣ። *ወንድሜ ወረቀት ፃፈልኝ* ።

ወረቀት አቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ አዘጋጅቶ በስብሰባ ላይ አነበበ፡ አሰማ ።

የወረቀት መብሻ ስ ወረቀትን ለመብሳት የሚያገለግል የፅህፈት መሳሪያ ።

የወረቀት ማቀፊያ ስ ብዙ ወረቀቶችን በአንድ ላይ አድርጎ ለመያዝ፡ ለማስቀመጥ የሚያገለግል የፅህፈት መሳሪያ ።

የወረቀት ገንዘብ ስ በወረቀት መልክ ታትሞ የተዘጋጀ ህጋዊ ገንዘብ።

ወረበ^{1} ግ በቢማ ወረብን አሰማ፡ አሸበሸበ ።

ወረብ ስ ምንባባዊ ይዘቱ አጠር ያለ ሆኖ ካህናት ከፀናፅል፡ ከከበሮ ጋር እያቀናበሩ የሚያለዝቡት፡ የሚወርቡት፡ የሚያሸበሽቡት መንፈሳዊ ዜማ ።

ወረበ^{2} ግ የካፊያ አይነት ዝናብ ጣለ፡ በመጠኑ መሬትን አረጠበ ።

ውርብ ስ ሌሊት መሬትን አርጥቦ የሚገኝ መጠነኛ የካፊያ አይነት፡ ጤዛ፡ ውርጭ፡ ርጥበት።

ወረብ "ወረበ^{1}" ስር ተመ.

ወረተኛ "ወረት^{2}" ስር ተመ.

ወረታ "ወሮታ" ን ተመ.

ወረት^{1} ስ 1. በእጅ ያለ ገንዘብ፡ ንብረት፡ ጥሪት። 2. እንደመነሻ ሆኖ ለንግድ ስራ የሚያገለግል ዋና ገንዘብ፡ ካፒታል።

ወረት^{2} ስ ፅናት ወይም መሰረት የሌለው ጊዜያዊ ፍቅር ።

ወረቱ አለቀ በአዲስነቱ የነበረው ፍቅር አለቀ፡ ሰለቸ ።

በወረት ሳይሰለች፡ በአዲስነቱ ጊዜ። *በወረት ብዙ ተበላ* ።

ወረተኛ ቅ 1. በአንድ የማይፀና፡ ፅኑ ፍቅር የሌለው፡ አንዴ ከአንዱ፡ አንዴ ከሌላው የሚሆን። 2. ፍቅሩ የማይቆይ ።

ወረንጦ ስ እሾህን ለማውጣት የሚያገለግል የብረት መቆንጠጫ።

ወረንጦ ቂጥ ቅ (ስድብ፡ ዘይ.፡ ቀጭን፡ የቂጣም ተቃራኒ ።

ወረንጦ አፍ ቅ (ስድብ) ነገረኛ ።

ወረወረ ግ 1. ጣለ፡ አሽቀንጥረ። 2. ሰደደ፡

ለቀቀ፡... (ቀስትን፡ ጦርን፡...)። 3. ዘጋ፡ ቆለፈ፡ ቀረቀረ (የበር፡ የመስኮት መቀርቀሪያን)። 4. አቀረበ፡ ሰነዘረ (ሃሳብን፡...)። 5. በንቀት፡ በጥላቻ፡...ሰጠ። *ከፊቴ ፈድፋጅ ብሎ ትንሽ ገንዘብ ወረወረለት*። 6. ማግን በድር መሃል በመወርወሪያ አስተላለፈ ። 7. በርካሽ ሸጠ። 8. ኸሮ አድርጎ ጣለ።

መወርወሪያ ስ 1. መቀርቀሪያ፡ መሸጎሪያ። 2. ማግን በድር መሃል ለማስተላለፍ የሚረዳ የሸማኔ መሳሪያ።

ተወረወረ ግ 1. ዘለለ፡ እንጣጥ ብሎ አለፈ፡ ተሸቀነጠረ (በአንድ ነገር ላይ ለማረፍ ወይም አንድን ነገር ለመያዝ)። 2. በፍጥነት ሄደ፡ ፈትለክ አለ ።

ተወርዋሪ ኮከብ ስ በምሽት ከሚታዩ ከዋክብት መሃል በድንገት ብልጭ ብሎ እየተወረወረ ሲጠፋ የሚታይ ኮከብ።

ተወርዋሪ ጦር ስ በድንገት እየደረሰ አደጋ የሚጥል ጦር።

ተወራወረ ግ 1. ወረወረ፡ ጣለ። 2. ስድብና ዘለፋን፡...ተለዋወጠ፡ ተመላለሰ።

ወረዛ ግ ራሰ፡ ርጥበት ያዘ ።

ወረዛት ስ የእንፋሎት ነጠብጣብ፡ ርጥበት።

አወረዛ ግ አረጠበ፡ አራሰ።

ወረደ ግ 1. ከፍ ካለ ቦታ ወደ ዝቅተኛ ቦታ ሄደ፡ ተጓዘ፡ ተንቀሳቀሰ። 2. መሬት ላይ አረፈ (ከዛፍ፡ ከመኪና፡...)። 3. ፈሰሰ። *እንባው ይወርዳል*። 4. ተባረረ፡ ተወገደ (ከማዕረግ፡ ከስልጣን፡...) ። 5. አነሰ፡ ዝቅ አለ። ሙቀቱ ወረደ ። 6. ረከሰ፡ ዋጋ ቀነሰ ። *የቡና ዋጋ ወረደ* ። 7. ደረሰ፡ ወደቀ። *ችግር ወረደበት*። 8. ተንዘረፈፈ፡ ረዘመ (ለምሳሌ. ፀጉር) ። 9. ሰፈነ፡ ተገኘ። *ሰላም ወረደ*። 10. ተላለፈ። *ከአባት ወደ ልጅ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ* ። 11. መታ፡ ጨፈረ (እስክስታን በአንገት፡ በትከሻ)።

መውረጃ ስ መሄጃ ፡ መተላለፊያ፡ መንገድ።

ወረደበት 1. ብዙ ተቆጣው፡ ዘለፈው፡ ሰደበው። 2. ብዙ በላ (ምግብ፡...) ።

ወረዳ ስ ከአውራጃ በታች ያለ የአስተዳደር ክፍል።

[የ]ወረዳ ወረደ ከማእረጉ፡ ከደረጃው ዝቅ ብሎ ያለብለጠው ጥለ ።

ወረዳ ምክር ቤት ስ በወረዳ ደረጃ የተቋቋመና የተወሰነ ስልጣን ያለው ምክር ቤት።

ወረዳ አስተዳዳሪ ስ የወረዳ አስተዳደር ከፍተኛ ባለስልጣን ።

ወረዳ ገዥ ስ የወረዳ ከፍተኛ ባለስልጣን ወይም አስተዳዳሪ የቀድሞ መጠሪያ ።

ወራዳ ቅ (ስድብ) ነውረኛ፡ ልክስክስ፡ ቅሌታም።

ወራጅ ቅ 1. የሚሄድ፡ የሚወርድ፡ የሚፈስ፡ ረግቶ ያልቆመ (ውሃ፡ ወንዝ፡...)። 2. ከተሳፈረበት መኪና ውስጥ የሚወርድ፡ ወደውጭ የሚወጣ። 3. ወደታች ሂያጅ፡ ተጓዥ። 4. የቤት ክዳን ቆርቆሮ የሚመታበትን ማገር የሚሸከም አቃልዳይ እንጨት፤ አውራጅ እየተባለም ይጠራል።

ወርድ ስ የጎን ስፋት ።

ውራጅ ቅ አሮጌ፡ ያገለገለ (ልብስ፡ ጫማ፡...)።

ውርደት ስ ቅሌት፡ አሳፋሪ ነገር ።

ውርዴ ቅ የቂጥኝ በሽታ ታሞ የዳነ ።

ውርድ ንባብ ስ ጎተት የሚልና በዜማ መልክ የሚነበብ የንባብ ቤት ትምህርት፣ የአነባበብ መንገድ ።

ውርድ ከራሴ በሚደርሰው ጉድለት፡ ጥፋት፡...እኔ አልጠየቅም ለማለት የሚነገር አባባል።

ውርጃ ስ የሽል፡ የፅንስ መጨንገፍ።

ውርጅብኝ ስ ቁጣ፡ መአት፡ድንገት የመጣ አደጋ።

ውርርድ ስ እንዲህ ነው፡ አይደለም፡ ይሆናል፡ አይሆንም በሚል በተለያየ ሃሳብና አስተያየት ምክንያት በሰዎች መካከል የሚደረግ ፉክክር (ተረቺ የሚሆነው ወገን የተወሰነውን ነገር ለመክፈል ቃል የሚገባበት ስምምነት)።

ውርርድ ተከለ ለውርርድ የሚሆን ገንዘብ አስያዘ፡ አስቀመጠ፡ መደበ።

ተወረደ ግ ፈፀመ፡ ጨረሰ፡ተወጣ። *እገሌ እዳውን ተወረደው*።

ተወራጅ ቅ አነስተኛ፡ ዝቅተኛ፡ ምክትል (ሹም)።

ተወራረደ ግ 1. ተፎካከረ፡ ቢረታ ወይም ቢሸነፍ በውርርዱ ጊዜ የተወሰነውን ነገር ሊከፍል ቃል ገባ፡ ተዋዋለ። 2. ተበለተ፡ ተቆረጠ (ስጋ)። 3. የወፌጪ ማስረጃው ቀርቦ ከወፌጪ ቀረው ተመለሰ።

ተወራራጅ ቅ ተፎካካሪ (በውርርድ) ።

ተዋረደ ግ 1. ከክብሩ ዝቅ አለ፡ ቀለለ፡ በሚያሳፍር ሁኔታ ተገኘ። 2. ተላለፈ (ካለፈው ወደሚቀጥለው፣...)። *ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ባህል*።

ተዋረድ ስ ከከፍተኛ ወደዝቅተኛ የሚሄድ፡ የሚወርድ ደረጃ፡ እርከን።

በተዋረድ በደረጃ፡ ከላይ ወደታች።

አወረደ ግ 1.አስወገደ፡ አስነሳ (ከስልጣን፡ ከማዕረግ)። 2. ከፍ ብሎ ከነበረበት ቦታ ወደታች አመጣ(ለምሳሌ. ፍራፍሬን ከዛፍ ላይ)። 3.

ከመኪና ፣ ከባቡር፥... ላይ አራገፈ (ሰውን ወይም እቃን)። 4. አሳነሰ ፣ ቀነሰ ፣ ዝቅ አደረገ። 5. አሰፈነ፤ አነገሠ፤ አሳደረ። *ሰላም አወረደ/በረከት አወረደ*። 6. በሆዳልና በከበሮ እየታጀበ በእቋቋም የዜማ ስልት መንገድ አዜመ፤ ዜማውን አንቆረቆረ፤ አሰማ። *ዚቅ አወረደ*። 7. አቀነቀነ፤ ዘፈነ፤ ዘፈን አውራጅ ሆነ። 8. አንጎደጎደ (ስድብን፤ ቁጣን፤...)። 9. አቃለለ፤ አራገፈ (ሸክምን፤...)። 10. በብዛት ሰጠ፥ አዘነበ። 11. ምድር ላይ ጣለ። *አውሮፕላኖችን በጥይት አወረደው*። 12. አነሳ፤ ሰረዘ (ዋስትናን፤ ሃላፊነትን)።

አውራጅ ስ 1. አቀንቃኝ፥ የዘፈን መሪ፥ ዘፋኝ። 2. እቃን፤ ሸክምን ከጭነት ላይ የሚያወርድ ሰው። 3. አቆልቋይ፤ ሞላላ የመቃ ወይም የሳንቃ ግበታ።4. የቆርቆሮ ቤት የጣሪያ ማገር ተሸካሚ እንጨት፤ ወራጅ ።

አዋረደ ግ 1. አቃለለ፤ ከማእረግ፤ ከክብር ዝቅ አደረገ። 2. ሰደበ፥ አሳፈረ፥ እፍረት ላይ ጣለ ።

አዋራጅ ቅ ተሳዳቢ፤ ባለጌ፤ ሰውን የሚያዋርድ፤ የሚያሳፍር።

አውራጃ ስ በስሩ የተወሰኑ ወረዳዎችን የያዘ የአስተዳደር ክፍል ።

አወራረደ ግ 1. የወጪ ማስረጃን በማቅረብና ቀሪውን ተመላሽ በማድረግ ሂሳብን ዘጋ። 2. አፎካከረ፥ እንዲወራረዱ አደረገ። 3. ቆረጠ፤ በስተ፥ ሰየፈ። 4. እየጠጣ፥ ፉት እያለ፥ እያረሰ በላ። *ምሳውን በሻይ እያወራረደ በላ* ።

ማወራረጃ ስ ምግብን በደንብ ለመብላት ወይም የተበላውን ለማንሸራሸር የሚረዳ መጠጥ።

አስወረደ ግ እንዲወርድ አደረገ።

አስወረደች ግ ሽሉ ፣ ፅንሱ ከማህፀኗ እንዲወጣ ፣ እንዲጨነግፍ አደረገች።

አስወረዳት ግ (ሽሉ ወይም ፅንሱ) ወጣባት፤ ጨነገፈች።

***ወረገረገ**

ተውረገረገ ግ ተረገረገ፥ የኩራት፥ የቄንጥ አረማመድ ተራመደ።

ተውረግራጊ ቅ የሚውረገረግ፥ የሚረገረግ።

ወረገኑ ስ ቀደም ሲል በነበረው ስርአት የመንግስትን የእርድ ከብቶች የሚቀልብ ሰው ወይም ከብቶቹ ይቀለቡበት የነበረ ቦታ ።

ወረጋ ቅ 1. ጓዝ የለሽ፤ ባዶ እጁን የሚጓዝ፤ የሚሄድ፤ ሌጣ (ተጓዥ)። 2. ያልተጫነ፤ ጭነት የሌለው (የጋማ ከብት) ።

ወረግቡ "ውር" ስር ተመ.

ወረጨ ግ ሁርጭን፤ አመዳይን ጣለ፤ በረደ፤ ቀዘቀዘ ።

ውርጭ ስ በቢጋ ወራት በአየር ቅዝቃዜ የተነሳ ሌሊቱን መሬት ወይም ሳር ላይ ተጋግሮ የሚገኝ ርጥበት ።

ውርጭ እንደደው ውርጭ መታው፤ ጎዳው።

ውርጭ ከከው ዝ.ከ.

***ወረጨ**

ተወራጨ ግ ተቅበጠበጠ፤ የጭንቅ እንቅስቃሴ ተንቀሳቀሰ፤ ተንፈራገጠ ።

አወራጨ ግ አቅበጠበጠ፤ እንፈራገጠ፤ እረፍት ነሳ።

ወረፈ ግ ሰደበ፤ ዘለፈ ።

ወራፊ ቅ ሰዳቢ፤ ዘላፊ ።

***ወረፈ**

ወረፋ ስ ለአንድ ጉዳይ አንድ ቦታ ላይ የተገኙ ሰዎች እንደአመጣጣቸው ቅደም ተከተል የሚጠብቁት ተራ ።

ወረፋ ነው/አለ ተራውን ይዞ የሚጠብቅ ብዙ ሰው አለ ።

ወረፋ ያዘ ተራ ያዘ፤ እንደአመጣጡ በቅደም ተከተል ተሰለፈ ።

ወረፍ ወረፍ አደረገ ግ አለፍ አለፍ እያለ፤ እየዘለለ ሰራ፤ አነበበ፤ አጨደ ።

ወሬሬ ቅ ገርጋራ፤ ደንባራ፤ በርጋጊ (ከብት) ።

ወረሳ ስ ድንገተኛ ወረራ፤ ዘረፋ ።

ወረሳ መጣ ድንገተኛ ወረራ፥ ዘረፋ አካሄደ።

አፈ ወረሳ ሳያስቡ ድንገት አፍ እንዳመጣ መናገር ።

ወራ ግ ቢጫ መልክ ያዘ፤ ቢጫ መሰለ ።

አወራ ግ ቢጫ አስመሰለ።

***ወሬ**

ወሬ ስ 1. በሰዎች መካከል የሚደረግ ጭውውት፤ ንግግር፤ እንዲሁ ለሌላው የሚያስተላልፈው የሃሳብ ልውውጥ (ብዙውን ጊዜ ተራ የሆነ)። 2. አዲስ የሚሰማ ነገር፤ ዜና። *ምን ወሬ አለ* ?

[ለ]ወሬ ነጋሪ አልቀረም ሁሉም አለቀ፥ ሞተ ወይም በቦታው የለም ።

ወሬ ለቀመ ወሬ ሰበሰበ ።

ወሬ ለቃሚ ቅ አሾክሻኪ፤ ከአንዱ ሰምቶ ለሌላ የሚያቀብል ።

ወሬ ነው ውሸት ነው፤ ያልተደረገ፤ ያልተፈፀመ፥ ያልተረጋገጠ ነገር ነው ።

ወሬ አቀበለ አንሾከሾከ፥ አሳበቀ፥ ነገር አቀበለ።

ወሬ አቀባይ ቅ ወሬን ከአንዱ ወስዶ ለሌላው የሚነግር፤ አሳባቂ ።

ወሬ አየ በአካባቢው የሚደረገውን፣ የተፈጠረውን ነገር ተመለከተ ።

ወሬ ዘረጋ ወሬ ያዘ፣ ቀጠለ ።

ወሬ ይቀዳል ወሬ ይሰበሰባል።

ወሬ ይቀጃል ወሬ ዘርግቷል፤ ወሬ በማውራት ወይም በማዳመጥ ላይ ነው ።

ወሬን ዘራ ወሬን አሰራጨ፣ ለሁሉ አዳረሰ።

ወሬው ተዛመተ/ዘመተ ወሬው በሰፊው ተሰራጨ፣ ተሰማ፣ ተዳረሰ።

ወሬው ደራ ወሬው ደመቀ፣ ሞቀ፣ እየጨመረ፣ እየሰፋ ሄደ ።

ወሬው ጠፋ ስለአንድ ሰው፣ ጉዳይ፣ ነገር፣... የሚሰማ ነገር ታጣ።

ወሬውን ይበልቃል ስራ ፈትቶ ያወራል ።

ወሬውን ይከስክሳል/ ይከካል/ ይከመኩማል ወሬውን በሰፊው እያወራ ወይም እያዳመጠ ይገኛል ።

ወሬ ምሳው ወሬ ወዳድ፣ ወሬኛ፣ ወሬ ካገኘ ለምሳው እምብዛም ግድ የሌለው ።

የወሬ አባት 1. ወሬውን መጀመሪያ ያወራው ወይም ያመጣው (ሰው)። 2. ወሬኛ ።

የወሬ ቋት ወሬ የሚወድ፣ የሚሰበስብና መልሶ የሚነዛ፣ በስራ የማይጠመድ ።

የወሬ ምንጭ ወሬውን በመጀመሪያ ያመጣ ወይም ያወራ ።

ወሬኛ ቅ 1. ወሬ የሚወድ፣ ብዙ የሚያወራ። 2. አሳባቂ፣ ወሬ አመላላሽ።

ተወራ ግ ተነገረ፣ ተባለ፣ ተሰራጨ (ወሬው) ።

አወራ ግ ነገረ፣ አሰራጨ፣ አስተላለፈ (ወሬን)።

አዋራ ግ 1. አናገረ። 2. አወራ ወይም አዳመጠ(ወሬን) ።

አስወራ ግ አስነገረ፣ እንዲዛመት ወይም እንዲሰራጭ አደረገ (ብዙውን ጊዜ የውሸት ወሬ)።

ወራረ "**መረረ**" ስር ተመ.

ወራሽ "**ወረሰ**"ን ተመ.

ወራት "**ወር**"ን ተመ.

ወራንታ ስ ከገራምጣ ወይም ከአክርማ፣... የሚሰራና ከቁና ከፍ የሚል የእህል መስፈሪያ ።

ወራውራን ስ በበጋ መጥለቂያ ጊዜ የሚታይ ደብዘዝ ያለ የፀሃይ ብርሃን ወይም የእሳት ወጋገን።

ወራዳ "**ወረደ**" ስር ተመ.

ወራጅ ዝ.ከ.

ወራፊ "**ወረፈ**" ስር ተመ.

ወሬ "*ወራ" ስር ተመ.

ወሬኛ ዝ.ከ.

ወር (ብ.ቁ.**ወራት**) ስ 1. ሰላሳ ቀናትን የሚይዝ የአመቱ አንድ አስራ ሁለተኛ ክፍለ ጊዜ (ለምሳሌ ከመስከረም አንድ እስከ መስከረም ሰላሳ ያለው ጊዜ አንድ ወር ነው)። 2. ሰላሳ ተከታታይ ቀናትን የያዘ የጊዜ መጠን። *መጋቢት 10 ቢመጣ ስራ ከጀመርኩ 1 ወር ይሞላኛል።*

ከወር እስከ ወር 1. ሁልቀን፣ ሁልጊዜ። *ከወር እስከ ወር እረፍት የለውም።* 2. ለወር ያህል ጊዜ። *ደመወዙ ከወር እስከ ወር ላያደርሰውም።*

ወረግቡ ቅ ልትወልድ የደረሰች፣ ዘጠነኛ ወሯን የያዘች (ሴት) ።

ወር ተራ ስ በየተራ ለወር ያህል የሚከናወን የስራ ፈረቃ፣ ጊዜ ።

ወር ተረኛ ቅ የወሩ ባለተራ (አንድን ተግባር ለማከናወን) ።

ወር አለፍ አንድ ወር እያለፉ በየሁለተኛው ወር (የሚደረግ፣...) ።

የወሩ (የወር) ነው የአመቱ አይደለም፣ አይነግስም፣ ታሪክ አይሰራም። *የተቀየሙት ሚካኤል የአመት መስሎን ነበር፤ ለካስ የወሩ ኖሯል ።*

የወር አበባ ስ በየወሩ እስከ ሰባት ቀናት ከሴቶች ማህፀን የሚፈስ ደም፣ አደፍም ይባላል።

የወር ክፍያ ስ በየወሩ የሚከፈል ገንዘብ (የአገልግሎት፣ የትምህርት፣ ...)።

ወርሃ __ የ __ ወቅት፣ ጊዜ። *ወርሃ ክረምት*።

ወርሃ ፅጌ ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ከመስከረም ሃያ ስድስት እስከ ህዳር ስድስት ቀን ድረስ ያለው የአበባ ጊዜ፣ ማርያም ልጇን ይዛ ከኢየሩሳሌም ወደ ግብፅ የተሰደደችበት ወራት መታሰቢያ ።

ወርሃዊ ቅ በየወሩ የሚደረግ፣ የሚወጣ፣ የሚታተም፣...።

ወርቅ ስ 1. ልዩ ልዩ ጌጣ ጌጦችን፣ ገንዘቦችን ለመስራት የሚያገለግል የከበረ ማእድን። 2. በሰም ተደብቆ፣ ተሸፍኖ የሚነገር የቅኔ ውስጠ ምስጢር። 3. (በዘ.) ጥሩ፣ ቆንጆ። *አለሙ ወርቅ ነው።*

በወርቅ ነደደ በወርቅ ተሸቆጠቆጠ፣ አጌጠ ።

ወርቀ ዘቦ ስ በወርቅ ፈትል የተጌጠ፣ የተጠለፈ (ካባ፣ ጋምጃ፣...) ።

ወርቃ ወርቅ ስ ሰሙን ትቶ በወርቁ ብቻ የሚነገር የቅኔ መንገድ፣ ሰም ረገፍ ።

ወርቅ ቀለም ስ በወርቅ የተለበጠ ወይም ወርቅን የሚመስል ቀለም ።

ወርቅ ቅብ ቅ ውስጡ ሌላ ሆኖ ላዩ ወርቅ

ወይም ወርቅ ቀለም የተቀባ፡ የተከላ (እቃ) ።

ወርቅ ሰሪ ስ ከወርቅ፡ ከብር፡...የተለያዩ ጌጦችን የሚሰራ ባለሙያ ።

ወርቅ በሚዶ ስ መድሃኒትነት አለው የሚባል፡ በመሬት ላይ ለጥፍ ብሎ የሚበቅል፡ ወርቅ የሚመስል ቅጠል ያለው የእፅዋት አይነት።

ወርቅ ውሃ ስ የወርቅ ቀለምን ለመበጥበጥ የሚያገለግል ፈሳሽ ።

ወርቃማ ቅ 1. ወርቅ የሚመስል፡ የሚያምር። 2. ጥሩ፡ ተፈላጊ፡ ውድ የሆነ። *ወርቃማ ጊዜ* ።

ወርቅዬ ስ ፍሬው ትልልቅ፡ ገለባው በቀላሉ የሚለቅ፡ ለቆሎና ለእንጀራ የሚሆን የገብስ አይነት።

የወርቅ ኢዮቤልዩ ስ የአንድ ድርጅት ሃምሳኛ አመት ክብረ በአል ።

የወርቅ ጥርስ ስ ሰው ሰራሽ የሆነ፡ ብዙውን ጊዜ በወለቀ ጥርስ ፈንታ የሚተከል ከወርቅ የተሰራ ጥርስ ።

የወርቅ ፍልቃቂ በጣም የሚያምር፡ ውብ፡ ቆንጆ ።

ወርች ስ የከብት የፊት እግር ስጋ ።

ወርች ከምብል ቅ ዘቅዛቃነት፡ ቁልቁለትነት ያለው፡ ተዳፋት (መሬት) ።

ወርካ "ዋርካ" ን ተመ.

ወርድ "ወረደ" ስር ተመ.

ወሮ በላ "ወረረ" ስር ተመ.

ወሮታ(ወረታ) ስ 1. ለመልካም ስራ የሚሰጥ፡ ለውለታ የሚከፈል ጥሩ ነገር፡ ሽልማት። 2. በጎ ስራ፡ ድርጊት፡ ውለታ ።

ወሰለተ(ወሳለተ) ግ ባለገ፡ ማገጠ፡ በስራ የማይገኝ ሆነ፡ ዋለገ ።

ወስላታ ቅ በቃሉ የማይገኝ፡ እምነት የማይጣልበት፡ አታላይ ።

ውስልትና ስ 1. አለመታመን፡ የሚታለል ድርጊት። 2. ማጋጣነት፡ ስራ ፈትነት ።

አወሰለተ ግ አማገጠ፡ አባለገ ።

ወሰራ[ዶሮ] ስ መላው አካሉ ነጭ ሆኖ ጅራቱ ወይም ክንፉ ላይ ቀይ ያለበት ዶሮ ።

ወሰሰ ግ ቀጠነ፡ መነመነ፡ ቀለለ (የስንዴ፡ የገብስ ፍሬ) ።

ወስስ ቅ ቀጭንና ቀላል የሆነ (የስንዴ፡ የገብስ ፍሬ) ።

***ወሰበሰበ**

ውስብስብ ቅ 1. የተጠላለፈ፡ ውትብትብ (ክር፡ ገመድ፡ መንገድ፡...)። 2. አስቸጋሪ፡ በቀላሉ ሊቃለል የማይችል። 3. በጣም የተመሰቃቀለ፡ ግልፅ ያልሆነ፡ በቀላሉ መረዳት የማይቻል።

ተወሳሰበ ግ 1. ተጠላለፈ፡ ተሳሰረ፡ በቀላሉ ሊለያይ ወይም ሊፈታ የማይችል ሆነ (ለምሳሌ ክር፡ ገመድ፡...)። 2. ረቀቀ (ሃሳብ፡ ነገር)። 3. አስቸጋሪ፡ ከባድ፡ በቀላሉ መፍትሄ ሊያገኝ የማይችል ሆነ። *ፈጣን እርምጃ ባለመወሰዱ ችግሩ ሁሉ ተወሳስቧል*።

አወሳሰበ ግ 1. አጠላለፈ፡ አቆላለፈ፡ እርስ በርስ አስተሳሰረ (ለምሳሌ ገመድን፡ ክርን)። 2. አስቸጋሪ፡ ከባድ፡ በቀላሉ የማይፈታ አደረገ (ችግርን፡...)።

ወሰነ ግ 1. አንድ ነገር እንዲፈፀም ወይም አንድ አይነት እርምጃ እንዲወሰድ ተስማማ፡ አቀደ፡ አሰበ። 2. ገደበ፡ ከለለ። 3. ደነገገ፡ ስርአትን አበጀ፡ ሰራ። 4. ቆረጠ፡ እንዲህ ይሁን አለ። *ቀን ወሰነ/ ዋጋ ወሰነ/ሃሳቡን ወሰነ* ።

ወሰን ስ 1. ድንበር፡ የቦታ፡ የሃገር ክልል። 2. ገደብ፡ መወሰኛ። *አንተን በማግኘቴ ደስታዬ ወሰን የለውም* ።

ወሰን ገፋ ከክልሉ፡ ከድንበሩ አልፎ የሌላውን ቦታ ያዘ።

ከወሰን ያለፈ እጅግ ብዙ።

ወሰንተኛ (ወሰነተኛ) ቅ ድንበርተኛ ።

ወሳኝ ቅ 1. የሚወስን፡ ውሳኔ የሚሰጥ። 2. ለውጤት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያለው፡ ከፍተኛ ሚና የሚጫወት። *ያንተ መገኘት ወሳኝ ነው*።

ውሱን(ውስን) ቅ 1. በጥቂት ነገሮች ብቻ የተገደበ፡እንደፈቀደው በሁሉም ቦታ የማይገኝ፡ ቁጥብ ። 2. ጥቂት፡ ብዙ ያልሆነ።

ውሳኔ ስ የተሰጠ ትእዛዝ፡ እንዲፈፀም፡ እንዲደረግ የተባለ ወይም በስብሰባ ወስነው ያሳለፉት ስምምነት።

ውሳኔ አስተላለፈ ውሳኔ ሰጠ።

ውሳኔ ህዝብ ስ ህዝብ ፍላጎቱን፡ ምርጫውን የሚገልፅበት መንገድ።

ተወሰነ ግ 1. ውሳኔ፡ ትእዛዝ ተሰጠ ወይም ተላለፈ፡ ውሳኔ አገኘ። 2. ተደነገገ። 3. ተገደበ፡ ተከለለ። 4. ተቆረጠ ፡እንዲህ ይሁን ተባለ።

የተወሰነ መጠነኛ ቁጥር ያለው። *የተወሰነ ህዝብ በስብሰባው ተገኝቷል/ ለተወሰነ ሰአት ተገናኝተን ነበር*።

ያልተወሰነ ጊዜ በዚህ ቀን ይሁን ተብሎ ገደብ ያልተሰጠው ወይም ቀጠሮ ያልተያዘለት ጊዜ።

ተዋሰነ ግ 1. ድንበርተኛ፡ ወሰንተኛ ሆነ። 2. ድንበር ተካለለ ፡ አበጀ።

ተዋሳኝ ቅ ድንበርተኛ፡ ወሰንተኛ።

አዋሰነ ግ 1. በድንበር፡ በወሰን ተገናኘ፡

በስተምእራብ በኩል ሱዳን ኢትዮጵያን ታዋስናለች። 2. አካለለ፡ ድንበር አበጀ።

አዋሳኝ ቅ ወሰንተኛ፡ ድንበርተኛ፡ በወሰን የሚገናኝ።

ወሰካ ስ ቃሬዛ።

ወሰከ ስ ቆሻሻ፡ እድፍ።

ወሰወሰ ግ 1. ጥብቅ ያልሆነ ስፌትን ሰፋ፡ ሸደሸደ። 2. እጅና እግሩን ቀስ ቀስ አንቀሳቀሰ፡ አወራጨ (ለመዋኘት)። 3. እረፍት ነሳ፡ ገፋፋ፡ በል በል አለ ።

ወስዋሳ ቅ 1. (ስድብ) አርፎ የማይቀመጥ፡ እርጋታ የሌለው፡ ቅክታክ። 2. ሰባቂ፡ ቀማኛ፡ ሌባ።

ተወስወሰ ግ 1. ጥብቅ ያልሆነ ስፌት ተሰፋ። 2. እረፍት አጣ፡ ተገፋፋ ።

ተወሳወሰ ግ ቀማኛ፡ ሌባ፡ ወስዋሳ ሆነ ።

አወሳወሰ ግ 1. አዘመረ፡ አፈናፈነ፡ አንቀሳቀሰ፡ አወሳዳ። *ዋስ አይወሳውስ* ። 2. አሳበቀ፡ አዋሸከ፡ ነገር አመላለሰ ።

ወሰው ቅ.አ. ድንቅ፡ ግሩም፡ መልካም፡ ጎሽ፡ እሰዬ ለማለት የሚነገር አባባል። *እጅግ ጠቃሚ ስራ ሰርቶ ነበር፡ ወሰው ያለው የለም እንጂ*።

ወሰደ ግ 1. ተቀበለ፡ ተረከበ። 2. ያዘ፡ በእጁ አደረገ። 3. ወደ አንድ ቦታ ይዞ ሄደ። 4. በላ ጠጣ... (ምግብን፡ መጠጥን፡ መድሃኒትን)። 5. ሰረቀ። *ንብረቱን ሌባ ወሰደው*። 6. ፈጀ፡ ጨረሰ፡ ያዘ። *ጊዜ ወሰደ/ብዙ ቦታ ወሰደ*። 7. አመራ፡ አደረሰ። *ወደ መ/ቤቱ የሚወስደው መንገድ ተዘግቷል*። 8. ቀነሰ፡ አነሳ። *ከሃያ ላይ አስር ሲወሰድ አስር ይቀራል*። 9. ቆጠረ፡ ገመተ። *ያደረግሃቸውን ሁሉ በክፋት ወሰደው*። 10. ያዘ፡ መዘገበ። *ስልክ ቁጥር ወሰደ/ንግግር ወሰደ*። 11. ተመለከተ፡ አየ፡ መረመረ። *ለምሳሌ ይህን ብንወስድ*።

ወሰድ ያደርገዋል 1. አእምሮውን ሳት ያደርጋል፡ ከትክክለኛው የአእምሮና የሃሳብ መንገድ ይወጣል። 2. አልፎ አልፎ ነገር ይዘነጋል፡ ይስታል።

ወሳጅ ስ ሰይጣን፡ ሰላቢ። *እህሉን ወሳጅ ወሰደው መሰለኝ አልበረከት አለ* ።

ወሳሰደ ግ በጥቂቱ ደጋግሞ ጠጣ (የአልኮል መጠጥን) ።

ተወሰደ ግ 1. በሌላ ሰው ቁጥጥር፡ እጅ፡ ይዞታ ስር ገባ። 2. ተይዞ ሄደ። *በፖሊስ ተወሰደ*። 3. ተሰረቀ። 4. ተፈጀ፡ ተጠቀመ። *ጊዜ ተወስዶ ከተሰራ በጥሩ ሁኔታ ያልቃል*።

ተወሰደለት ተነሳ፡ ተቀነሰ (ከላዩ) ።

ተወሰደበት 1. ተቀማ፡ ተወረሰበት። 2. ተሰረቀ ።

አስወሰደ ግ እንዲወሰድ አደረገ።

ወሲብ ስ በወንድና በሴት መካከል የሚፈፀም ፍትወተ ስጋዊ ስራ፡ ግብረ ስጋ።

ወሲባዊ ግንኙነት የግብረ ስጋ ግንኙነት።

የወሲብ ፍላጎት የግብረ ስጋ ፍላጎት ።

ወሲፋ(ወሲፍ) ስ ኮረዳ፡ ወጣት፡ ልጅ እግር።

ወሳ

ተወሳ ግ 1. ተባለ፡ ተነገረ፡ ታተተ። 2. ታወሰ፡ ታሰበ፡ ተነሳ (ነገሩ፡...)።

አወሳ ግ 1. አተተ፡ ተናገረ። 2. አስታወሰ፡ አነሳ (ነገሩን፡...)።

ወሳለተ "ወሰለተ" ን ተመ.

ወሳሰደ "ወሰደ" ስር ተመ.

ወሳብሬ ስ የግመል ጊደር ።

ወሳኝ "ወሰነ" ስር ተመ.

ወሳጅ "ወሰደ" ስር ተመ.

ወሳፍቻ(መሳፍቻ) ስ እንደ ወስፌ ያለ የሌማ፡ የጅራፍ፡ የከርቻ፡...መስፊያ።

ወስላታ "ወሰለተ" ስር ተመ.

ወስከምቢያ(ወስከምባይ) ስ ከገራምጣ ወይም ከአክርማ...የሚሰፋ የሲሜት፡ የመሶብ፡... መክደኛ።

ወስከምት ስ 1. የውሻ ማሰሪያ፡ ማነቆ። 2. መቃጥን፡ የአሳ ማጥመጃ ቆላፋ ብረት። 3. ጅንጉላ።

ወስዋሳ "ወሰወሰ" ስር ተመ.

ወስፈንጥር

ወስፈንጥር ስ 1. ጎበጥ ካለ እንጨት የሚሰራ የወፍ፡ የቆቅ፡... መምቻ፡ ወጥመድ። 2. እንደጠፍር ያለ ሆኖ ጫፍና ጫፉ ባላንትብለው አንሰተኛ እንጨት ላይ የታሰረና ልጆች ጠጠር አጉርሰው እያስፈነጠሩ ወፎችን፡... የሚመቱበት ተለማጭ ጎማ ወይም ላስቲክ፡ ወንጭፍም ይባላል።

ወስፋት ስ 1. ቀጭን፡ ረጅም የሆነ የውስጥ ትል። 2. አንድን ነገር በጥሩ ስሜት የማድረግ፡ የመቀበል፡ የመውሰድ፡... ፍላጎት (ብዙውን ጊዜ ከመብላትና ከመጠጣት ጋር ተያይዞ የሚነገር)።

ወስፋቱ ተቆለፈ /እምቢ አለ/

አልቀበል አለ የምግብ ፍላጎት አጣ፡ አልበላለት አለ ።

ወስፋታም ቅ 1. (ስድብ) ወስፋት ያለበት፤ ወስፋት የያዘው። 2. ብዙ ምግብ የሚይበላ፤ የምግብ ፍላጎት የሌለው። 3. ቀጫጫ ።

ወስፌ ስ እንደ መሶብ፤ ሙዳይ፤... የመሳሰሉትን የስፌት እቃዎች ለመስፋት የሚያገለግል ቀጭንና ሹል ብረት።

ወስፌ ቂጥ ቅ 1. (ስድብ፤ ዘይ.) አንድ ቦታ አርፎ የማይቀመጥ፤ ቅንዝንዝ። 2. የቂጣም ተቃራኒ ።

ወሸለ ግ እንደ ነገሩ ሳያጠብቅ አሰረ።

ወሻላ ቅ ውትፍትፍ፤ ውሽልሽል፤ ጠበቅ ያልሆነ።

ውሽልሽል ቅ ጥብቅነት የሌለው፤ ልል ።

ተውሸለሸለ ግ ተውተረተረ፤ ጥብቅነት የሌለው ሆነ ።

አውሸለሸለ ግ አውተረተረ፤ እንደ ነገሩ ሰራ፤ ሳያጠብቅ አሰረ ።

ወሸለከ ግ 1. አሊያዝ፤ አልጨበጥ አለ፤ ሸለከ። 2. ወሰለተ ።

ወሻላካ ቅ (ስድብ) ወስላታ፤ ቁም ነገር የሌለው፤ የማይጨበጥ ።

ወሸላ ስ 1. ያልተገረዘ የወንድ ብልት። 2. (ዘይ.) ፈሪ፤ ወኔ የሌለው።

ወሸመ ግ ውሽማ ያዘ፤ አደረገ፤ ሚስቱ ካልሆነች ሴት ጋር በወዳጅነት፤ በፍቅር ተሳሰረ።

ውሽማ ስ በጋብቻ ያልታሰረ ድብቅ የግብረ ስጋ ግንኙነት ያለው ወዳጅ፤ ፍቅረኛ።

ተወሸመ ግ ውሽማ ሆነ።

ወሸቀ ግ አንድን ነገር በሌላ ነገር ውስጥ ሸጎጠ፤ ሻጠ፤ አገባ፤ ወተፈ ።

ወሻቃ ቅ (ስድብ) 1. የማይደፍር ፡ ፈሪ፤ ተልካሻ። 2. ልክስክስ፤ ወታፋ ።

ውሽቅ አለ ግ 1. በአንድ ነገር ውስጥ ድብቅ፤ ሽጉጥ ብሎ ተቀመጠ ። 2. ወደ ውስጥ ገባ፤ ተሸጎጠ።

ተወሸቀ ግ 1. ተሸጎጠ፤ ወደ ውስጥ ገባ ። 2. ተደበቀ፤ ተሸሸገ።

ተወሸቆ ዋለ ወደ ውጪ ሳይወጣ ከቤት ውስጥ ዋለ ።

ወሸባ[1] ስ 1. ጥቅልል፤ ሽብልል፤ ቀጭን የማግ አመልማሎ ። 2. መልከ መልካም፤ ሎጋ ።

ወሸባ[2] **(ውሽባ)** ስ ህመምተኛ የሆነ ሰው በተወሰነ ስፍራ ተገልሎና ከሰው ተለይቶ በመቀመጥ የሚያደርገው ባህላዊ የህክምና አይነት።

ወሸባ (ውሽባ) ገባ ከሰው ተለይቶና በተወሰነ ቦታ ቤት ዘግቶ በመቀመጥ በባህላዊ መድሃኒት ታከመ (በእፅዋት በመታጠን፤ በመታጠብ፤...)።

ወሸን ቅ ደግ፤ ማስፈያ።

ወሸኔ ቅ ውብ፤ ቆንጆ።

***ወሸከ**

አዋሸከ ግ አሳበቀ፤ ነገር አቀበለ።

አዋሻኪ ቅ አሳባቂ፤ ነገር የሚያቀብል።

ወሸከሬ ቅ (ስድብ) የማይረባ፤ ተልካሻ ።

ወሸከተ ግ የሆነ ያልሆነውን አወራ፤ እውነቱንና ሃሰቱን እየደባለቀ ተናገረ፤ ለፈለፈ፤ ቀላመደ።

ወሸካታ ቅ (ስድብ) የሆነ ያልሆነውን የሚያወራ፤ ውሸታም ፤ ቀባጣሪ።

ተወሻከተ ግ የሆነ ያልሆነውን አወራ፤ ዋሸ፤ ቀላመደ ፥ ወሸከተ።

ወሸገረ ግ ወለገደ፤ ጠመመ።

ወሸጋራ ቅ ወንጋራ፤ ወልጋዳ።

ተወሻገረ ግ ተወናከረ፤ ተወላገደ።

አወሻገረ ግ አወናከረ፤ አወላገደ።

ወሻቃ "ወሸቀ" ስር ተመ.

ወሸ ስ የላም ጡት (እንደ ከረጢት ያለው የወተት መያዣው)።

ወሻላካ "ወሸለከ" ስር ተመ.

ወሽመጥ ስ 1. ከብብት እስከ ሙሃይት ያለ ገላ። 2. የጠበበ ልብስን ለማስፋት በስላች ተቆርጦ የሚገባ ጨርቅ፤ ሰላጤ።

ወሽመጥ ቆረጠ ተስፋ አስቆረጠ።

ወሽማዳ ቅ (ስድብ) ውልክፍክፍ፤ ወልጋዳ።

ወሽካታ "ወሸከተ" ስር ተመ.

ወሽጋራ "ወሸገረ" ስር ተመ.

ወቀረ ግ 1. የወፍጮ ድንጋይን አተባ፤ አሻከረ፤ እንዲፈጭ አዘጋጀ። 2. ለቤት ህንፃ የሚሆን ድንጋይን ቀረፀ፤ አዘጋጀ፤ ጠረበ። 3. ነቀሰ (ጥርስን)። 4. አሰለጠነ፤ ትምህርት የሚያገባው ተማሪ እንዲገባው ጥረት አደረገ።

መዋቅር ስ 1. ከዋልታ እስከ ጣሪያ የሚወርድ ዋና ዋና የጣሪያ እንጨት፤ ወራጅ። 2. አንድ ድርጅት የተመሰረተበት ልዩ ልዩ ክፍሎችና ውስጣዊ ግንኙነታቸው፤ አደረጃጀታቸው።

መዋቅር ዘረጋ ልዩ ልዩ ድርጅቶችን በየደረጃው መሰረተ፤ አቋቋመ፤ አደራጀ ።

ውቃሪ ቅ 1. ከተወቀረ ወፍጮ የሚወጣ የድንጋይ ድቃቂ። 2. እህል ከተከካ በኋላ የሚቀር ድቃቂ ።

ውቅር ቅ 1. የጣራ ውጥን፤ ጅምር። 2. የተወቀረ (የድንጋይ ወፍጮ፤...)።

ውቅራት ስ ንቅሳት፥ ጥቁራት ።

ተወቀረ ግ 1. ተባ፡ ሻከረ(የወፍጮ ድንጋይ)። 2. ተጠረበ፡ ተቀረፀ (ድንጋይ)። 3. ተነቀሰ (ጥርስ)። 4. እንዲሰለጥን፡ ትምህርት እንዲገባው ተደረገ (ተማረ)።

ተዋቀረ ግ 1. ተወጠነ፡ ተጀመረ፡ ተሰራ (ጣራው)። 2. ተመሰረተ፡ ተደራጀ፡ ተቀናበረ።

አዋቀረ ግ 1. ወጠነ፡ ጀመረ፡ ሰራ (ጣራውን)። 2. መሰረተ፡ አደራጀ፡ አቀናበረ ።

ወቀሬ ስ አጋሰስ፤ የኮርቻ ፈረስ ያልሆነ ።

ወቀሰ ግ 1. ባለፈ የተደረገን ጥፋት በማንሳት፡ በማስታወስ ገሰፀ፡ ነቀፈ። 2. የተፈጸመበትን በደል፡ የተሰማውን ሃዘን፡ ቅሬታ፡...እያነሳ በደሉን ሳያደርስበት ወገን በምሬት ተናገረ፡ በደለኝ አለ ።

ወቀሳ ስ 1. ነቀፋ፡ ተግሳፅ፡ ምክር። 2. በደል የተፈፀመበት ሰው የሚያሰማው የሃዘን፡ የቅሬታ፡ የቁጭት፡ የፀፀት፡ የብሶት ቃል፡ እሮሮ ።

ተወቀሰ ግ 1. ተተቸ፡ ተገሰፀ፡ ተመከረ (ባደረሰው ጥፋት፡ በደል)። 2.ወቀሳ ቀረበበት ።

ተወቃሽ ቅ 1. ጥፋተኛ፡ በደለኛ ተደርጎ የሚቆጠር። 2. ወቀሳ የሚቀርብበት ወይም የቀረበበት (አጥፊ፡ በደል ፈፃሚ)።

አስወቀሰ ግ 1. አስነቀፈ፡ አስተቸ። *ይህ ድርጊት ያስወቅሰናል*። 2. በደለኛ፡ ጥፋተኛ አስደረገ።

ወቀጠ(ወገጠ) ግ 1. እህልን ወይም ሌላ ነገርን በሙቀጫ ውስጥ አድርጎ ሸከሸከ፡ አደቀቀ። 2. በሃይል መታ፡ ደበደበ። 3. ቀጠቀጠ፡ አኮላሸ (የከብትን አባለዘር)።

መውቀጫ ስ የሙቀጫ ማለገል፡ ዘነዘና ።

ሙቀጫ(ሙገጫ) ስ በአንድ ጫፉ በኩል መሃሉ ከተቦረቦረ ግንድ የሚዘጋጅና በዘነዘና አማካኝነት እህልና የመሳሰሉት ነገሮች ውስጡ ተጨምረው የሚወቀጡበት የቤት እቃ።

ሙቀጫ

ሙቀጫ ቂጥ (ስድብ) ቂጠ ትልቅ።

ሙቀጫ እግር ስ (ስድብ) ከቁርጭምጭሚት እስከ ጉልበት ያበጠ፡ የወፈረ እግር ያለው።

የሙቀጫ ልጅ ስ ዘነዘና።

ውቅጥ ስ 1. በሙቀጫ የተወቀጠ ፡ ያልላመ በርበሬ፡ ውቅጥ በርበሬም ይባላል። ቅ 2. የተኮላሸ (እንሰሳ)።

ተወቀጠ ግ 1. እህል ወይም ሌላ ነገር ሙቀጫ ውስጥ ተደርጎ ተሸከሸከ፡ ደቀቀ። 2. በሃይል ተመታ፡ ተደበደበ። 3. ተኮላሸ፡ ተቀጠቀጠ (የከብት አባለዘር)።

ወቃ ግ 1. አበራየ፡ የእህልን ነዶ አውድማ ላይ በርግዶ ፍሬው ከአገዳው ወይም ከገለባ እስኪላቀቅ ድረስ ከብቶች በላዩ ላይ እየዞሩ መላልሰው እንዲረግጡት በማድረግ፡ በከብት እግር ፍሬው ከገለባው ያልተለየውን ወይም መጠኑ አነስተኛ የሆነን የእህል ነዶ በዱላ በመቀጥቀጥና ፍሬውን ከገለባው በመለየት ምርቱን ሰበሰበ። 2. አጋድሞ መታ፡ ደበደበ። 3. በሃይልና በብዛት ጣለ ወይም ዘነበ። *ዝናቡ ወቃው*።

ውቂያ ስ እህልን የመውቃት፡ የማበራየት ስራ።

ተወቃ ግ 1. ፍሬው ከአገዳው ወይም ከገለባ እስኪላቀቅ ድረስ የእህል ነዶ አውድማ ላይ ተበርግዶ ከብቶች በላዩ ላይ እየዞሩ መላልሰው እንዲረግጡት ከተደረገ በኋላ ከገለባው እየተለየ ምርቱ ተሰበሰበ። 2. በሃይል ተመታ፡ ተደበደበ።

ተዋቃ ግ በዱላ ተደባደበ ።

ወቄራ ስ ካራ፡ ቢላዋ ።

ወቄት ስ የወርቅ ክብደት መለኪያ (አንድ ወቄት 28 ግራም ነው)።

ወቅሰምት(መቅሰምት) ስ ቢላዋ፡ ካራ ።

ወቅት ስ 1. በአየሩ ሁኔታ መለዋወጥ መሰረት ከተመደቡት የአመቱ አራት ክፍለ ጊዜያት እንዱ የሆነው፡ በጋ፡ የፀደይ፡ የክረምት ጊዜ። 2. ጊዜ፡ ሰአት። *በበልግ ወቅት የሚዘራን ዘር በወቅቱ እንድንዘራ መፍጠን አለብን*።

የወቅቱ ሁኔታ በአሁን ጊዜ ያለው ሁኔታ ።

ወቅታዊ ቅ 1. አሁን ያለው። *ወቅታዊ ሁኔታ*። 2. ጊዜያዊ፡ በቋሚነት የሌለው። *ወቅታዊ ችግር*።

ወበራ^{1} ስ ሰዎች በተራ የሚያካሂዱት የመረዳዳት ስራ፡ ደቦ ።

ወበራ^{2} ግ 1. ወገሸ፡ በረየ። 2. ቀበጠ፡ ተቀናጣ።

ወባራ ቅ ቀበጥ ።

ተወበራ ግ ተቀናጣ፡ ቀበጠ ።

ወበራ^{3} ግ ገረጣ፡ ደረቀ፡ ለመታጨድ ደረሰ (የገብስ፡ የስንዴ፡...ሰብል) ።

ወበቀ ግ ጋለ፡ ሞቀ፡ ተኮሰ፡ ላብ ላብ አለ ።

ወበቅ ስ ሙቀት (የአየር) ።

ወባ ስ በትንኝ አማካኝነት የሚተላለፍ፡ ትኩሳት ያለውና የሚያንቀጠቅጥ የበሽታ አይነት ።

የወባ ትንኝ ስ የወባ በሽታን የምታስተላልፍ፡ አብዛኛውን ጊዜ በቆላ አካባቢ የምትገኝ ትንኝ ።

ወባት ስ ለተቸገረ የሚቆም ጠበቃ ።

ወባት ገባ ለተጨነቀ፡ ለተቸገረ ጥብቅና ቆመ፡ ረዳ፡ አገዘ።

ውበራ "ወበራ^{2}" ስር ተመ.

ወበሸማኔ(አበሸማኔ) ስ ነብር የሚመስል

በቢጫ መደብ ጥቁር ጠቃጠቆ ያለበት የዱር አውሬ(ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።

***ወተረ**

ውትርትር ቅ 1. ለመራመድ የሚፍጨረጨር፣ የሚንተረተር። 2. አልፎ አልፎ የተተከለ፣ የተታታ (አጥር፣ የቤት ጣራ፣...) ።

ውትር ውትር አለ ግ 1. ከአቅም ማነስ፣ ከለመቻል የተነሳ እየተንገዳገደ ለመራመድ፣ ለመሄድ ሞከረ። 2. ተፍጨረጨረ፣ ተንተረተረ።

ተውተረተረ ግ 1. ተፍጨረጨረ፣ ተንተረተረ። 2. አልፎ አልፎ ተተከለ፣ ተታታ።

አውተረተረ ግ 1. የግድግዳን፣ የአጥርን እንጨት አልፎ አልፎ ተከለ፣ አያየዘ። 2. እንደ ነገሩ ለመስራት ሞከረ፣ ተፍጨረጨረ፣ አውተፈተፈ።

ወተር ስ የሸረሪት ድር ።

አውታር ስ 1. የጅልባ፣ የድንኳን፣ የተስት መወጠሪያ ገመድ። 2. የድርጅት፣ የተቋም፣ ... የተሳሰሩ ቅርንጫፎች። *ድርጅቶቹ ብዙ የማከፋፈያ አውታሮችን ዘርግተዋል* ።

***ወተበተበ**

ውትብትብ ቅ የተውተበተበ፣ የተሳሰረ፣ የተያያዘ፣ የተጠላለፈ ።

ተውተበተበ ግ ተሳሰረ፣ ተያያዘ፣ ተጠላለፈ።

አውተበተበ ግ አስተሳሰረ፣ አያያዘ፣ አጠላለፈ።

ወተት ስ 1. አጥቢ እንስሳት ልጆቻቸውን በጡት አማካይነት የሚመግቡት ወይም በተፈጥሮ ከሚገኘው ጋር ተመሳሳይ ይዘት እንዲኖረው ተደርጎ በዱቄት መልክ የሚሰራና ተበጥብጦ የሚጠጣ ነጭ ፈሳሽ። 2. ከቁልቋል፣ ከትንጭብ ወይም ከሌላ እፅዋት የሚወጣ ነጭ ፈሳሽ።

ወተት ነው (ዘይ.) 1. የጥሁ፣ ንፁ ነው። 2. ቀላል ነው። *ፈተናው ወተት ነው* ።

ወተት ይመስላል በጣም ነጭ ነው ።

ወተቴ ስ ገራም የሆነች የፈንጣጣ አይነት የምትጠራበት የቁልምጫ ስም ።

ወተት አንጀት ስ የአንጀት አንዱ ክፍል ።

የወተት ጥርስ ስ ሌላ በማብቀል የሚተካ ጊዜያዊ የልጅነት ጥርስ ።

ወተወተ ግ 1. ያለማቋረጥ ለፈለፈ፣ ብዙ አወራ። 2. ጎተጎተ፣ ደጋግሞ ተናገረ፣ አሳሰበ ።

ውትወታ ስ ጉትጎታ ።

ወተፈ ግ 1. ጨርቅን ወይም ሌላ ነገርን በመክተት ቀዳዳን፣ ሽንቁርን ደፈነ። 2. ሻጠ፣ አስገባ፣ ቀረቀረ ።

ወታፋ ቅ 1. (ስድብ) አቅመ ቢስ፣ ደካማ። 2. ከተጠጋበት ቤት የማይወጣ፣ የማይጠፋ ።

ውታፍ ስ 1. የጠርሙስ አፍ ወይም የሌላ ሽንቁር ነገር መክደኛ። 2. የሌላውን ሰው ስራ ለመሸፈን በምትክነት የገባ ወይም የሚገባ ።

ውትፍትፍ(ወተፍታፋ) ቅ የማይረባ፣ ውሽልሽል ስራ።

ውትፍትፍ አለ ግ ውሽልሽል አለ፣ ጥብቀት የሌለው ሆነ ።

ተወተፈ ግ 1. ተሸጎጠ፣ ተከደነ። 2. ገባ፣ ተቀረቀረ ።

ተወታተፈ ግ ጥብቀት በሌለው፣ በማይረባ ሁኔታ ተሰራ ።

ተውተፈተፈ ግ የማይረባ፣ መናኛ፣ ጥብቀት የሌለው ስራ ሆነ ።

አውተፈተፈ ግ ጥብቀት በሌለውና በማይረባ አኳኋን ሰራ ።

ወታብ ስ 1. እንደ ቁና ባለ ቅርፅ ከጭድ ተዘጋጅቶና በእበት ተለቅልቆ ለእህል፣ ለጥራጥሬ መያዣ ወይም ማስቀመጫ የሚሆን እቃ። 2. (ስድብ) ክፍት አፍ። 3. (ዘይ.) መልከ ጥፉ፣ ቅርፀቢስ፣ ፉንጋ።

ወታደር ስ በፖሊስ ወይም በጦር ሰራዊት ውስጥ ገብቶ የሚያገለግል መለዮ ለባሽ ።

ወታደራዊ ቅ በወታደሩ ክፍል ያለ ወይም የሚካሄድ፣ የወታደር። *ወታደራዊ ሰልፍ*።

ወታደራዊ መንግስት ስ ከወታደሩ ክፍል ተውጣጥቶ የአገሪቱን አመራር በሃይል በመያዝ የሚቋቋም መንግስት ።

ወታደራዊ ሰላምታ ስ ወታደር እጁን ወደ ግንባሩ አስጠግቶ በማውጣት የሚያሳየው የአክብሮት መግለጫ፣ ሰላምታ ።

ወታደራዊ ሰልፍ ስ የወታደሩ ክፍል በልዩ ልዩ የጦር መሳሪያዎች እየታጀበ የሚያሳየው የሰልፍ ትርኢት ።

ወታደራዊ ትምህርት ስ መከላከልን፣ ጠላት ማጥቃትን፣ የውጊያ ስልትን የመሳሰለ ትምህርት።

ወታደራዊ አስተዳደር ስ ህዝባዊ ውክልና በሌለው የወታደሩ ክፍል የበላይነት የሚካሄድ የሃገር አስተዳደር ።

ወታደራዊ አገዛዝ ስ ከወታደሩ ክፍል የወጡ ጥቂት ሰዎች የመንግስት ስልጣን በሃይል ከነጠቁ በኋላ የሚያካሂዱት የሃይልና የጭቆና አስተዳደር ።

ወታደራዊ ካምፕ ስ የወታደሩ ክፍል አባላት የሚሰበሰቡበት፣ ትምህርት የሚያካሂዱበት፣ የሚኖሩበት፣ መሳሪያ የሚያስቀምጡበት ግቢ፣ ካምፕ።

ወታደራዊ ጣልቃ ገብነት ስ በሌላ ሃገር

ጉዳይ ውስጥ በጦር ሃይል ጭምር የሚደረግ ጣልቃ ገብነት ፡፡

ወታፋ "ወተፈ" ስር ተመ .

ወትሮ ተውሳ 1. ቀድሞ፡ በፊት፡፡ 2. ዘወትር፡ ሁልጊዜ ፡፡ *ወትሮ በዚህ ሰዓት እዚህ ይገኝ ነበር፡፡*

ያለወትሮው ያለልማዱ፡፡ *ያለወትሮው ዛሬ በጧት መጣ ፡፡*

ወነበደ ግ 1. ወንበዴ፡ ቀማኛ፡ ዘራፊ ሆነ፡፡ 2. ስራ ፈት፡ ዘዋሪ፡ ዱርዬ ሆነ፡፡ 3 ደነበረ፡ ሸሸ፡ ሮጠ፡ አመለጠ (ከብት) ፡፡

ወንበዴ ስ ቀማኛ፡ ዘራፊ፡ ሽፍታ ፡፡

ውንብድና ስ ሽፍትነት፡ ቅሚያ፡ ዝርፊያ ፡፡

ተወነባበደ ግ ተሳሳተ፡ ተምታታ፡ ተዘበራረቀ፡ ተደነጋገረ፡፡

ተወናበደ ግ 1. ተደናበረ፡ ተደናገረ፡፡ 2. ተሳሳተ፡ ተምታታ ፡፡

አወናበደ ግ 1. አደናበረ፡ አደናገረ፡፡ 2. አሳሳተ፡ አምታታ፡ አዘበራረቀ፡፡ 3. የሃሰት ወሬ፡ ፕሮፓጋንዳ ነዛ ፡፡

አወናባጅ ቅ አታላይ፡ አዘበርባሪ ፡፡

***ወነከረ**

ወንካራ ቅ ሲሄድ የሚንገዳገድ፡ የሚወላገድ፡ ድክድክ የሚል ፡፡

ውንክርክር ቅ ውልግድግድ ፡፡

ተወናከረ ግ 1. ተወላገደ፡ ተንገዳገደ፡ ተውተረተረ፡፡ 2. አቋቋሙ የተወላገደ ሆነ (ግድግዳው፡ አጥሩ፡...) ፡፡

አወናከረ ግ አወላገደ፡ አውተረተረ፡፡

***ወነወነ**

ውን ውን አለ ግ ተንቀነቀ፡ ተወዘወዘ ፡፡

ውን ውን አደረገ ግ አወዛወዘ፡ አንቀነቀ ፡፡

ተወናወነ ግ ተወዛወዘ፡ ተንቀነቀ ፡፡

አወናወነ ግ አወዛወዘ፡ አንቀነቀ (ጅራቱን)፡፡

ወነጀለ ግ በጥፋት፡ በወንጀል ከሰሰ፡ በደለኛ አደረገ (በሃሰት ወይም በእውነት) ፡፡

ወንጀል ስ 1. ህገወጥ የሆነ ተግባር (እንደ ሌብነት፡ ግድያ፡...የመሳሰለ)፡፡ 2. ጥፋት፡ በደል፡ ስህተት ፡፡

ወንጀል ሰራ-/ፈፀመ ህገወጥ የሆነ ድርጊት፡ ጥፋት ፈፀመ ፡፡

የወንጀል ችሎት ስ የወንጀል ክስ የሚታይበት ችሎት ፡፡

ወንጀለኛ ስ የወንጀል ድርጊት፡ ጥፋት የፈፀመ ሰው (ስርቆት፡ እምነት ማጉደል፡ ግድያ፡...)፡፡

ወንጀለኛ መቅጫ [ህግ] ስ የወንጀል አይነቶችንና የሚያስከትሉትን ቅጣት የሚዘረዝር ደንብን ወይም ህግን የያዘ መፅሃፍ፡፡

ወንጃይ ቅ 1. ከናኝ፡ ስም አጥፊ፡፡ 2. ከሳሽ፡፡

ተወነጀለ ግ ህግ በመጣስ፡ ወንጀል በመፈፀም ተከሰሰ፡ በደለኛ፡ ጥፋተኛ ተባለ፡፡

አስወነጀለ ግ አስጠየቀ፡ አስከሰሰ፡፡ *ሰዎችን ለማዳን ያደረጉት አያስወነጅለንም፡፡*

ወነገ ግ ወዘወዘ፡ እንቋለጠ፡፡

ውንግ ውንግ አለ ግ ተወዘወዘ፡ ተንቀነቀ፡፡

ተወነገ ግ ተወዘወዘ፡ ተንቀነቀ (ከወገቡ፡ ከጅራቱ፡...) ፡፡

***ወነጠ**

ውንጥ ውንጥ አለ ግ ውልምጥ ውልምጥ አለ፡፡

ተወነጠ ግ ተወነገ፡ ተወዘወዘ፡፡

ወነጨፈ ግ ድንጋይን በወንጭፍ ወረወረ፡፡

ወንጭፍ ስ 1. ከክር ወይም ከገመድ የሚሰራ የድንጋይ መወርወሪያ፡፡ 2. የ"**ወስፈንጥር**"ን 2ኛ ፍቺ ተመ.

ወንጭፍ

ተወነጨፈ ግ ተወረወረ፡ ፈጥኖ ሄደ፡ አለፈ፡ ተራመደ፡ ተምዘገዘገ ፡፡

ተወናጨፈ ግ 1. ተወራጨ፡ ተፈራገጠ፡፡ 2. ተወረወረ፡ ተምዘገዘገ፡ ተፈናጠረ ፡፡

አወናጨፈ ግ 1. አወራጨ፡ አፈራገጠ፡፡ 2. ወረወረ፡ አምዘገዘገ፡ አፈናጠረ ፡፡

***ወነፈለ**

ወንፈል ስ በገጠር አካባቢ በየተራ የሚደረግ የመረዳዳት ስራ፡ ደቦ (በግብርና፡ በፈትል፡...)፡፡

ወንፈል አወጣ ቀደም ሲል በስራ ያገዘውን ወይም የረዳውን ሰው በተራው አገዘ፡ ረዳ፡ ብድሩን መለሰ፡፡

ወንፈለኛ ቅ ወንፈል ያለበት፡ የወንፈል ስራ ማህበርተኛ፡ በበኩሉ ባለተራውን በስራ የሚረዳ፡፡

ተወናፈለ ግ በየተራ በስራ ተረዳዳ (የግብርና፡የፈትል፡...ስራን በመስራት)፡፡

አወናፈለ ግ አገዘ፡ የወንፈል ስራን ሰራ፡፡

ወና (ኦና) ቅ ባዶ፡ ምንም የሌለበት (ቤት፡ ቦታ)፡፡

ወና ሆነ ባዶ ሆነ (ቤት፡ ቦታ)፡፡

ወናሄ ስ ፍሬው ነጭ የሆነ የዛፍ አይነት ፡፡

ወናሄ ይመስላል ነጭ ነው፡፡ *ፀጉሩ ወናሄ ይመስላል፡፡*

ወናፍ ስ 1. ጩበጥ ለቀቅ ሲያደርጉት ወደ ውስጥ

አየሩን መልሶ በሚያስወጣው የአየር ማፊት የእጅ ባለሙያዎች (ቢላዋ፣ ማረሻ…ሰራተኞች) ብረታ ብረቶችን ለማጋል የሚጠቀሙበትን ከቆዳ የሚያፍሱበት፣ የአየር ማስገቢያና ማስወጫ ሁለት ቧንቧ የተገጠመበት ስልቻ። 2. (ዘይ.) ወሬኛ ።

ወኔ ስ ድፍረት፣ ልበ ሙሉነት፣ አስፈሪ ነገርን መከራን ለመጋፈጥና ለመቋቋም የሚያስችል የቆራጥነት ስሜት።

ወኔ የለውም ቆራጥነት፣ ድፍረት የለውም፣ ፈሪ ነው።

ወኔው ሸና ፈራ፣ ሐሞቱ ፈሰሰ ።

ወኔው ተቀሰቀሰ ቆራጥነት፣ የጀግንነት ስሜቱ ተነሳ

ወኔ ቢስ ቅ ፈሪ ቆራጥነት፣ ድፍረት የሌለው ።

ወንበላ ስ በቆላና በወይና ደጋ የሚበቅል፣ ግንዱ ለማገዶነት የሚያገለግል ዛፍ ።

ወንበር ስ 1. ከእንጨት፣ ከብረት…የሚሰራ፣ ለመቀመጫነት የሚያገለግል እቃ። 2. ዳኛ (ለምሳሌ - የግራ ወንበር፣ የቀኝ ወንበር)። 3. ከኋላ በመቀመጫ በኩል ያለ የተንፋነፋ ስጋ ክፍል። 4. ትምህርት። *ወንበር ተዘርግቷል*።

ወንበር ተከለ (ቤ.ክ.) ማስተማር ወይም መማር ያዘ ፣ ጀመረ።

ወንበር ተዘረጋ (ቤ.ክ.) ትምህርት ተጀመረ።

ወንበር ታጠፈ (ቤ.ክ.) የትምህርት ጊዜ አበቃ ፣ አቆመ።

ወንበር ዘረጋ **"ወንበር ተከለ"** ን ተመ.

ወንበር ያሞቃል ያለምንም ስራ ተቀምጦ ይውላል።

ወንበር ገፋ በሌተረው ያልተሰራውን፣ ያላሟላውን ስራ ተከታዩ ተረኛ አሟላ፣ሰራ።

ወንበር ገፍ (ገፊ) ስ በተረኛው ምትክ የሚሰራ፣ የሚከፍል ተከታይ ተረኛ ።

ወንበርተኛ ስ (ቤ.ክ.) አንድ አይነት ትምህርት በአንድነት አብሮ የሚማር የትምህርት ጓደኛ።

ወንበዴ **"ወንበደ"** ስር ተመ.

ወንከራ **"*ወነከረ"** ስር ተመ.

ወንዘረዬ ስ ጅራቱ ረጅም ወፍ።

ወንዝ ስ ተፈጥሮአዊ የሆነ፣ በሰፊ ቦይ እየወረደ ወደ ሐይቅ፣ ወደ ባሕር… የሚገባ ወይም ከሌላ ወንዝ ጋር የሚቀላቀል ወራጅ ውሃ።

ወንዝ አድምቅ ስ በወንዝ ዳር፣አካባቢ የሚበቅል የእፀዋት አይነት።

የወንዝ ልጅ የአካባቢ፣ የአገር ልጅ።

የወንዝ እምቴ ስ ረዥም ያለ ቅልጥምና መንቁር ያለው፣ መልኩ ጥቁር ቡናማ የሚመስል፣ በወንዝ አካባቢ የሚገኝ የአሞራ አይነት(ስእሉን አሞራ ስር ተመ.)።

ወንድ ቅ 1. ከሴት የሚለይበት ተፈጥሮአዊ የፆታ ምልክቶች (ለምሳሌ ፂም ወይም ሌሎች መለያዎች) ያሉት ሰው ወይም ሌላ ሕያው ፍጡር፣ እንስሳ። 2. (ዘይ.) ጎበዝ፣ ጀግና ።

ወንድ ጠጣው ስ ጎበዝ፣ በርታ ።

ወንደላጤ ስ ያላገባ ወንድ ።

ወንዳ ወንዴ ስ ማጠፊያ የሌለው የገጠር ቤት ግንድ (መጋጊያ) ከላይ ከጉበኑ፣ ከታች ከደፉ ላይ ተሰክቶ በመቆም ያለችግር እንዲከፈትና እንዲዘጋ የሚረዳ፣ በግንዱ የላይና የታች ጠርዝ ላይ እንደ ቀንድ ሾል ሾል ተደርጎ የሚሰራ የግንዱ አካል ።

ወንዳ ወንድ ቅ 1. ወንድ፣ ጀግና። 2. በሰውነት አቋሟ ወይም በባህርይዋ ወንድ የምትመስል ሴት።

ወንዳ ገረድ ስ 1. የወንድና የሴት ተፈጥሮአዊ የፆታ ምልክት ያለው፣ ፍናፍንት። 2. (ስድብ) ሴታሴት የሆነ ጠባይ ያለው ወንድ ።

ወንድ አያት ስ የእናት ወይም የአባት አባት።

የወንዶች ገና ስ የገና በአል የሚከበርበት እለት (ወንዶች የገና ጨዋታ የሚጫወቱበት ስለሆነ የወንዶች ገና ተባለ) ።

ወንዲላ ቅ በቅርፅ ወይም በጠባይ የወንድ ባህርይ ያላት፣ ወይም የቤት ባልትና የሌላት (ሴት)።

ወንዴ ቅ የወንድ ፆታ ያለው (ለሰው፣ ለእንስሳም ሆነ ለእፅዋት ይነገራል) ።

ወንድም ስ 1. አንድ ሰው ከእናቱ ወይም ከአባቱ ወይም ከሁለቱም ከሚወለደው ወንድ ልጅ ጋር ያለው ዝምድና መጠሪያ። *ሊጅቱ ከእናትና ከአባቷ የተወለደ አንድ ወንድም ብቻ አላት*፡ 2.የአክስት ወይም የአጎት ወይም የቅርብ ዘመድ ወንድ ልጅ። 3. እንደ እናት ልጅ የሚቆጠር ጥሩ ጓደኛ። 4. በእድሜ ተመጣጣኝ የሆነን ወይም አነስ የሚልን ሰው በአክብሮት ለመጥራት የሚያገለግል ቃል። *ወንድም ስንት ሰአት ነው?*

ወንጀለኛ **"ወንጀለ"** ስር ተመ.

ወንጀል ዝ.ከ.

ወንጃይ ዝ.ከ.

ወንጌል ስ በሃዲስ ኪዳን ውስጥ ከተፃፉትና ስለኢየሱስ ክርስቶስ ታሪክ፣ ትምህርትና ተአምራት ከሚተርኩት የመጀመሪያዎቹ አራት መፃህፍት አንዱ ወይም አራቱ።

ወንጌላዊ(ብ.ቁ.**ወንጌላውያን**) ስ የወንጌል መምህር፣ ሰባኪ።

ወንጠፍት ስ እንደ ወንፊት ሆኖ የሚሰራ ለፈሳሽ ማጥለያነት የሚያገለግል እቃ፡ ማጥለያ፡፡

ወንጭፍ "ወነጨፈ" ስር ተመ.

ወንፈለኛ "*ወነፈለ" ስር ተመ.

ወንፊል ዝ.ክ.

ወንፊት ስ 1. እህልን ወይም ዱቄትን ለመንፋትና ተፈላጊውን ከማይፈለገው ለመለየት የሚያገለግል ከአክርማ፡ ከሸንደቆ፡ ከሣራምባ ወይም ከሽቦ ተታትቶ የሚሰራ እቃ፡፡ 2. ዘዴኛ፡ ወሬኛ ፡፡

ወከለ ግ ለንብረቱ ወይም ለስራው እንደ ራሱ ሆኖ እንዲሰራለት የሚተማመንበትን ሰው መርጦ መደበ፡ ተካ፡ ሃላፊ አደረገ፡፡

ወኪል ስ እንደ ዋናው ሆኖ የሚሰራ ተጠሪ፡ ሃላፊ፡ ዋናውን ተክቶ እንዲሰራ የተመረጠ ሰው፡ አካል ፡፡

ውክልና ስ ለአንድ ሰው ወይም ድርጅት ወኪል፡ ተጠሪ መሆን ፡፡

ተወከለ ግ 1. ተጠሪ፡ ወኪል ሆነ፡፡ 2. አንድን ህዝብ ወክሎ በምክር ቤት፡ በሰበሰባ...ተገኘ ፡፡

ተወካይ ቅ አንድን ግለሰብ፡ ድርጅት፡ ሃገር፡ ህዝብ፡ ... የሚወክል ተጠሪ ፡፡

***ወከበ**

ተዋከበ ግ ተጣደፈ፡ ተቻኮለ፡ ግራ ተጋባ ፡፡

አዋከበ ግ አጣደፈ፡ አቻኮለ፡ ግራ አጋባ ፡፡

ወከከ

ወከክ አለ ግ 1. ተሰነጠቀ፡ ተተረተረ፡፡ 2. በድንጋጤ ወይም በደስታ ልቡ ተሰነጠቀ፡ ክው አለ፡፡

ወኪል "ወከለ" ስር ተመ.

***ወካ**

ውካታ(ዋካታ) ስ መደማመጥ የሌለበት፡ የብዙ ሰው ንግግር፡ ወሬ፡ ጫጫታ ፡፡

ተዋካ ግ እርስ በርሱ እየተንጫጫ፡ ሳይደማመጥ አወራ፡ ተነጋገረ ፡፡

አወካ ግ አወራ፡ ተንጫጫ፡ ሳይደማመጥ ተነጋገረ ፡፡

አውካካ ግ እየተሳሳቀ፡ እየተንጫጫ አወራ፡ ተጫወተ ፡፡

ወዘላ ስ የአካል፡ የቁመና ውበት፡፡

ወዘበሬታ ስ ቧልት፡ የጨዋታ፡ የቀልድ ንግግር፡፡

ወዘተ ግ 1. ሆዱን ወይም ሌላ ነገርን ለማሞቅ በጣሳ፡ በማንቆርቆሪያ፡ በማሰሮ፡... እሳት ዳር አስቀመጠ፡ ጣደ፡፡ 2. ተሰርቶ ማለቅ የሚገባውን ሳይሰራ አስቀመጠ፡ ወዘፈ፡፡

ወዘት ስ የእሳት ዳር ወይም የምድጃ ሙቀት፡፡

ውዝት ቅ ከተቀመጠበት የማይነሳ፡ ውዝፍ፡ ሰነፍ፡፡

ተወዘተ ግ 1. እንዲሞቅ፡ እንዲሸቅ ወይም እንዲበስል በማሰሮ፡ በጣሳ፡... ተደርጎ በእሳት ዳር ተቀመጠ፡ ተጣደ፡ 2. ሳይንቀሳቀስ ስራ ፈቶ ተቀመጠ፡ ተጎለተ፡ ተወዘፈ፡፡

ወዘተረፈ በአህጽሮት ሲፃፍ ወዘተ. ተመ.ግ. የመሳሰሉት፡ የተቀሩትም ለማለት የሚያገለግል ቃል፡ *አልኮል ነክ የሚባሉ መጠጦች አረቄ፡ ኮኛክ፡ ወዘተ. ናቸው፡፡*

ወዘና ስ ውበት፡ ደምግባት፡ ለዛ፡፡

ወዘናቢስ ቅ ቸክ፡ ለዛቢስ፡

ወዘወዘ ግ 1. ነቀነቀ፡ 2. አንገላታ ..

ውዝዋዜ ስ የእስክስታ፡ የዳንስ እንቅስቃሴ፡፡

ተወዘወዘ ግ ተነቀነቀ፡ ወዲህ ወዲያ አለ፡ ሄደ፡ ተንቀሳቀሰ፡፡

ተወዛወዘ ግ 1. ተወዘወዘ፡፡ 2. እስክስ አለ፡ ደነሰ፡፡

ተወዛዋዥ ቅ 1. ተንቀሳቃሽ፡ ወዲያ ወዲህ እያለ የሚንቀሳቀስ፡፡ ስ 2. እስክስታ ወራጅ፡ ደናሽ፡፡

አወዛወዘ ግ አነቀነቀ፡ ወዲያ ወዲህ አንቀሳቀሰ፡፡

ወዘፈ ግ 1. ጎለተ፡ አስቀመጠ፡፡ 2. በየጊዜው ሳይፈጽም አስቀመጠ፡ አከማቸ (ስራን)፡፡

ወዛፍ ቅ 1. ስራ የማይሰራ፡ ዝም ብሎ መቀመጥ የሚወድ ሰነፍ፡ 2. በአጥር መልክ እንዲያገለግል እየተቆረጠ የተጋደመ እሾህማ እንጨት፡፡

ውዝፍ ቅ 1. (ለድብ) ሰነፍ፡ ከተቀመጠበት የማይነሳ፡፡ 2. ሳይከፈል የቀረ፡ የተጠራቀመ፡፡ *ውዝፍ እዳ*፡ 3. ያልተሰራ ወይም ሳይሰራ የቀረ (ስራ)፡፡

ተወዘፈ ግ 1. ተጎለተ፡ ተቀመጠ፡፡ 2.በጊዜው ሳይከፈል ተጠራቀመ (እዳ)፡፡ 3.በየጊዜው ሳይሰራ፡ ሳይከናወን ቆየ፡ ተቀመጠ (ስራ)፡፡

ወዛ ግ 1. ወዙ ወይም ላቡ ወረደ፡ ፈሰሰ፡፡ 2. ቅባት የተቀባ መሰለ፡፡

ወዝ ስ ፊት ላይ ወይም ሌላ ነገር ላይ ቅልጥልጥ ብሎ የሚታይ ላብ፡ ቅባት፡፡

ወዝ የሌለው የማይጥም፡ ደስ የማይል (ጨዋታ፡ ንግግር፡...)፡፡

ወዝ አደር "ላብ አደር" ን ተመ.

ወዛም ቅ መልኩ ያወለወለ፡ ያማረበት፡፡

ተወዛዛ ግ ቅባት ተቀባ፡ ተዋበ፡፡

አወዛ ግ ወዝ ሰጠ፡ በቅባት አሳመረ ።

***ወዛገበ**

ውዝግብ ስ ንትርክ፡ አተካራ፡ ጭቅጭቅ ።

ተወዛገበ ግ ተጨቃጨቀ፡ ተጣላ፡ ተነታረከ።

አወዛገበ ግ አጣላ፡ አጨቃጨቀ፡ አነታረከ።

አወዛጋቢ ቅ አጨቃጫቂ፡ አነታራኪ። *ጉዳዩ አወዛጋቢ እየሆነ ሄደ።*

ወገዛ "ወዛ" ስር ተመ.

ወየበ ግ 1. ቢጫ ሆነ። 2. ወደ ቢጫነት ተለወጠ፡ ተበላሸ ጠነበለ ።

ወይባ ስ 1. ቢጫ ቅርፊት ያለው የዛፍ አይነት። 2. ቢጫ ቀለም የተነከረ የባህታዊ ልብስ።

ወይባ ቀለም ስ ቢጫ ቀለም።

ወየው(ወዮ) የሃዘን ስሜት መግለጫ ቃል። *ጓደኛው የሞተ እለት ወየው እያለ ሲያለቅስ ነበር።*

ወያኔ ስ 1. ሸፍቶ በረሃ የገባ አመፀኛ፡ ወሮ ወማሽ 2. ለግዳይ ሲል ወሮነት የሚፈፅም ሰው።

ወይ¹ አንድ ሰው የሌላውን ሰው ስም በሚጠራበት ጊዜ ተጠሪው አቤት፡ እሰይ፡ ለማለት ለጠሪው የሚመልሰው ወይም የሚያሰማው ቃል ጠሪው ልጅ ወይም የእድሜ ጓደኛ ካልሆነ ግን በወይ ፋንታ አቤት ወይም እመት ይባላል (በማቀላመጥ ለመናገር "ወዬ" ይባላል)።

ወይ² የጥያቄ ማቅረቢያ ቃል። *ልጁ መጣ ወይ?* መገረምን፡ አድናቆትን መግለጫ ቃል። *ወይ ጉድ/ ወይ ግሩም።* 2. የ"**ወይም**"ን ፍቺ ተመ.

ወይ ነዶ እንዴት ያናድዳል።

ወይኔ የጭንቀትና የቁጭት ስሜትን ለመግለፅ የሚነገር ቃል። *ወይኔ ተበላሸሁ/ወይኔ ጉድ መጣብኝ!*

ወይ ጉድ መገረምን፡ መደነቅን ለመግለፅ የሚነገር ቃል። *ወይ ጉድ! የሰው ልጅ ጨረቃ ላይ ወጣ!*

ወይም(ወይንም፡ወይ) መስ. አማራጭን ለመጥቀስ የሚያገለግል ቃል፡ ለጥያቄ ሲሆን "ወይስ" ይሆናል። *ቀዩን ወይም ጥቁሩን ብርጭቆ ስጠኝ /ወይ እኔ ወይ አንተ እንሄዳለን/ ትመጣለህ ወይስ ትቀራለህ?*

ወይራ ስ 1. ጨፌ ሲጋን፡ ለእንስራ፡...ማገዶ እንጨት ለተለያዩ ተግባር የሚውል ጠንካራ ዛፍ። 2. (ዘይ.) ብርቱ፡ ጠንካራ ሰው።

የወይራ ዘይት ስ ከወይራ የሚገኝ ዘይት።

ወይስ "**ወይም**"ን ተመ.

ወይበ "ወየበ" ስር ተመ.

ወይና ደጋ ስ በቆላና ደጋ መካከል የሆነ፡ አየሩ ቀዝቃዛና ነፋሻነት ያለው አካባቢ፡ አገር።

ወይና ሟጭት ስ ለመድሃኒትነት የሚያገለግል የሚበላ፡ ሽታ ያለው የእፅዋት አይነት።

ወይኔ "ወይ²" ስር ተመ.

ወይን ስ ተጠምጣጣና በብዛት እጅብ ብለው ወይኖች የሚንዠረገጉ ጣፋጭ ፍሬዎችን የሚያፈራ፡ በቆላና በወይና ደጋ አካባቢ የሚገኝ፡ ግንዱ እንደሃረግ ያለ ስለሆነ ራሱን ችሎ የማይቆም የተክል አይነት፡ ፍሬውም ወይን ይባላል።

ወይና ቅ ወይንማ፡ የበሰለ የወይን ፍሬ የመሰለ ቀለም ያለው ።

ወይን ጠጅ ስ 1. ከወይን ጭማቂ የሚዘጋጅ መጠጥ። ቅ 2. የበሰለ ወይን የሚመስል ቀለም ያለው ።

የወይን ዘለላ ስ በአንድነት እጅብ ብለው በቅርንጫፎቹ ላይ የተንዠረገጉ የወይን ፍሬዎች ስብስብ።

ወይንማ ቅ የወይን ፍሬ የሚመስል ቀለም ያለው፡ ወደ ሰማያዊነት የሚያደላ የሃምራዊ ቀለም አይነት።

ወይንም "**ወይም**"ን ተመ.

ወይንጠጅ "**ወይን**" ስር ተመ.

ወይኖ ዝ.ክ.

ወይዘሮ (ብ.ቁ. **ወይዛዝርት**) ስ ያገባች ሴት የምትጠራበት የአክብሮት ስም።

ወይዘሪት ስ ያላገባች ሴት የምትጠራበት የአክብሮት ስም።

ወይድ "*ወገደ" ስር "**ወግድ**" ን ተመ.

ወይጉድ "ወይ³" ስር ተመ.

ወይፈን ስ ከጥጃ ከፍ፡ ከበሬ አነስ ያለና ያልተቀጠቀጠ ወንድ ከብት ።

ወዮ "**ወየው**" ን ተመ.

ወደ መዋ. መድረሻን ለመጠቆም የሚያገለግል ቃል። *ወደ አዲስ አበባ ሄደ /ወደ ማታ እመጣለሁ።*

ወደለ¹ ግ ወፈረ፡ ጠበደለ ።

ወደላ ቅ [illegible] ጠብደል፡ ወፍራም ።

ወደል ዝ.ክ.

አወደለ ግ አወፈረ፡ አጠበደለ ።

ወደለ² ግ ከኮርቻ ሄዶ ጫነ፡ አሰረ።

ወደሳ ስ 1.ከኮርቻ በስተኋላ የሚውል፡ ከበቅሎና ከፈረስ ጅራት ስር የሚገባ፡ ከወደመታጠፊያው በኩል በጠርቻ ትልታይ ወይም

በለስላሳ ቆዳ የተሸፈነ፣ የተደጋገሰለ ጠፍር፣ አቡን ዘለብ። 2. የጋማ ከብቶች ጭነት በሚጫኑበት ጊዜ ከጅራታቸው ስር የሚገባው ጠፍር ፡ ሰቢቃ።

ውዴላ ስ ከኩርቻ ደገሩ በስተኋላ የምትታሰር እንስተኛ ጭንቅ ።

ወደላ "**ወደለ**¹" ስር ተመ.

ወደል ዝ.ከ.

ወደመ ግ ጠፋ፣ አለቀ፣ አልም አለ፣ ተበላሸ።

አወደመ ግ አጠፋ፣ ጨረሰ፣ አበላሸ።

ወደረ ግ 1. እንዳይሄድ ወይም እንዳይራገጥ የከብት እግርን አሰረ፣ ቀየደ። 2. ሳበ፣ ወጠረ፣ ጎተረ ።

ወደሮ ስ ገመድ።

ተወደረ ግ 1. የከብት እግር እንዳይሄድ፣ እንዳይራገጥ ታሰረ፣ ተቀየደ። 2. ተሳበ፣ ተወጠረ፣ ተጎተረ።

***ወደረ**

ወደረኛ ቅ 1. ተተካካይ፣ ተመሳሳይ፣ ተነፃፃሪ፣ ተወዳዳሪ። 2. ተቃራኒ፣ ተፃራሪ ።

ወደረኛ መስተፃምር ስ (ሰዋ.) ራሳቸውን ችለው መቆም የሚችሉ አረፍተ ነገሮችን የሚያጣምር፣ የሚያያይዝ፣ የሚያቀናጅ ቃል ወይም ምእላድ (ለምሳሌ. አበበና ወርቁ ነገ ይመጣሉ ፣እኔ ረጅም ነኝ፣ እሱ ግን አጭር ነው። በሚሉት አረፍተ ነገሮች ውስጥ 'ና' እና 'ግን' ወደረኛ መስተፃምር ናቸው ።

ወደር ቅ አኩያ ፣ አቻ። *ወደር የለውም።*

ውድድር ስ ፉክክር፣ ለአንድ ነገር የሚደረግ ሽሚያ።

ተወዳደረ ግ ተፎካከረ።

አይወዳደርም የላቀ፣ የበለጠ ነው። *የስለላ ችሎታው ከማንም አይወዳደርም።*

ተወዳዳሪ ቅ 1. አቻ። 2. ተፎካካሪ ። *ተወዳዳሪ የለውም* ።

አወዳደረ ግ 1. አነፃፀረ፣ አስተያየ። 2. አፎካከረ።

ወደሮ "**ወደረ**" ስር ተመ.

***ወደሰ**

መወድስ ስ 1. ባለስምንትና ባለዘጠኝ ቤት የሆነ የቅኔ አይነት። 2. (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) እሁድ እሁድ ሌሊት በቤተክርስቲያን የሚዜም፣ የሚደረስ የምስጋና ዜማ።

ውዳሴ ስ ብዙውን ጊዜ ለአምላክ የሚቀርብ ምስጋና፣ ሙገሳ ።

ውዳሴ ከንቱ ስ ተገቢ ያልሆነ ምስጋና፣ ሙገሳ።

ተወደሰ ግ ተመሰገነ፣ ተሞገሰ ።

አወደሰ ግ አመሰገነ፣ አሞገሰ ።

ወደቀ ግ 1. በሌላ ሃይል ምክንያት ወይም የራሱን ሚዛን ባለመጠበቅ ከላይ ወደታች በመውረድ እምድር ላይ አረፈ፣ ተጋደመ፣ ተፈጠፈጠ። 2. ደከመ፣ ከሰረ፣ ተንኮታኮተ (በንግድ በኢኮኖሚ…) ። 3. ዋጋው ቀነሰ፣ ረከሰ። 4. አረፈ። *የቤተሰቡ ሃላፊነት እርሱ ላይ ወደቀ።* 5. ወደሚቀጥለው ደረጃ ሳይሸጋገር ቀረ። *ተማሪው በትምህርቱ ወደቀ።* 6. በሰው ወይም በአካባቢው ላይ ደረሰ፣ መጣ፣ ወረደ (አደጋ፣ በሽታ፣ መከራ…)። 7. ተቀባይነት አጣ። *በድምፅ ብልጫ ሃሳቡ ወደቀ።* 8. ተሻረ፣ አገልግሎት መስጠት አቆመ። 9. አረጀ፣ በእድሜ ገፋ። 10. ተዘረፈ (ወንበር)። 11. ቀጥ፣ ጠንከር፣ ፈርጠም ብሎ የነበረው ላላ፣ ተኛ (ጡት) ።

ወድቀህ ተነስ የሚለው የለውም የሚያስብለት፣ የሚቆረቆርለት፣ የሚረዳው በሆነ ጊዜ፣ ወዳጅ የለውም ።

ወድቆ ቀረ የሚያነሳው፣ የሚያስታምመው አጣ።

የወደቀበት አይታወቅም ጠፍቷል፣ የት እንዳለ አይታወቅም ።

መውደቂያ ስ መጠጊያ፣ መኖሪያ፣ መጠለያ።

ወዳቂ ቅ 1. አገልግሎት የሌለው፣ የሚጣል። 2. ወደሚቀጥለው ደረጃ ሳይሸጋገር የቀረ። 3. ተቀባይነት ያጣ።

ወዳቃ ቅ አቅመቢስ ።

ውዳቂ ቅ 1. የተጣለ፣ ቆሻሻ። 2. (ስድብ) የማይረባ፣ ተልካሻ። 3. የበከተ፣ ጥንብ ።

ውድቅ ቅ ተቀባይነት ያጣ። *ያቀረበው ሃሳብ ውድቅ ሆነበት ።*

ውድቀት ስ ክስረት።

ውድቅት ስ እኩለ ሌሊት፣ ጥቅጥቅ ያለ ጨለማ።

ተዋደቀ ግ ታገለ፣ ተጋደለ፣ ተሟሟተ (ለሀገሩ፣ ለነፃነት…)።

አዋደቀ ግ አራከሰ፣ ዋጋ አሳጣ፣ አቀለለ፣ አንኳሰሰ።

ወደብ ስ ለመርከብ መቆሚያና ማራገፊያ የተዘጋጀ የባህር ዳርቻ።

የወደብ ኪራይ ስ ለወደብ አገልግሎት የሚከፈል ግብር።

ወደቴ ቅ አውደልዳይ፣ ስራፈት፣ ዘዋሪ።

ወደነ ግ ሁለት ሁለቱን ሸክም ወይም ጭነት እያቀናጀ አሰረ፣ አቆራኘ፣ ቀረቀበ ።

ውድን ቅ ሁለት ሁለት እየሆኑ የታሰረ፣

የተቆራኘ ሸክም ወይም ጭነት፤ ቅርቃብ ::

ተወደነ ግ ታሰረ፥ ተቆረቆበ ::

ወደዚህ(ወዲህ) መዋ. ተናጋሪው ወዳለበት ቦታ፥ አቅጣጫ ::

ወደዚያ(ወዲያ) መዋ. 1. ከተናጋሪው ራቅ ብሎ ያለ ቦታ፥ አቅጣጫ:: 2. በኋላ:: *ካሁን ወዲያ እንደዚህ እንዳታደርግ* ::

ወደደ ግ 1. አፈቀረ፥ ፈቀደ:: 2. ፈለገ፥ ደስ አለው:: *ችግራቸውን ሊያቃልልላቸው ይወዳል*::

ሳይወድ በግድ ተገድዶ፥ በግዴታ:: *ገንዘቡን ሳይወድ በግድ ይከፍላል*::

ወዶ ሰጠ ሳይገደድ በፈቃዱ ሰጠ ::

ወዶ ዘማች ስ ግዴታ ሳይኖርበት በፈቃዱ የዘመተ ሰው ::

ወዶ ገባ ቅ 1. ግዳጅ ሳይኖርበት በፈቃዱ ሌላ ሰው ቤት ገብቶ የሚኖር (ለምሳሌ ውሻ):: ስ 2. በተፈጥሮ ለዛቢያነት ተስማሚ ሆኖ የተገኘ እንጨት (የዶማ፥ የመጥረቢያ፥... እጀታ)::

ወዳድ ቅ በጣም የሚወድ:: *ገንዘብ ወዳድ*::

ወዳጅ ስ 1. ባልንጀራ፥ ጓደኛ:: 2. ፍቅረኛ፥ ውሽማ:: ቅ 3. አፍቃሪ፥ የሚወድ::

ውዴታ ስ ፈቃደኝነት፤ ግዳጅ የሌለበት አድራጎት::

የውዴታ ግዴታ ስ በራስ ፈቃደኝነት የሚገቡት ግዴታ::

ውድ ስ 1. ፍቅር:: 2. ፈቃድ:: *ያለውድ በግድ*:: ቅ 3. ዋጋው ከፍተኛ የሆነ፤ እንደልብ የማይገኝ:: 4. ተወዳጅ፥ ተፈቃሪ::

በውድም በግድም በፈቃደኝነትም ሆነ በመገደድ፥ በማንኛውም መንገድ::

ወደድ አለ ግ ዋጋው ከፍ አለ፥ ጨመረ፥ ናረ::

ተወደደ ግ 1. ተፈቀረ:: 2. ዋጋው ጨመረ፥ ናረ::

ተወዳጅ ቅ ተፈቃሪ:: *ለተወዳጁ ወንድሜ*::

ተዋደደ ግ 1. ተስማማ፥ ግጥምጥም አለ (መጥረቢያው፥... ከዛቢያው ጋር):: 2. ተፋቀረ::

አዋደደ ግ 1. አስማማ፥ አገጣጠመ (ዛቢያውን ከመጥረቢያው ጋር):: 2. ዋጋ ከፍ አደረገ ::

አስወደደ ግ ዋጋን ከፍ አደረገ ::

ወዲህ "ወደዚህ"ን ተመ.

ወዲያ "ወደዚያ"ን ተመ.

ወዲያው ተው.ግ. 1. በፍጥነት፥ ከመቅፅበት:: *ከሄደበት ቦታ ወዲያው ተመለሰ*፡ መዋ. 2. በዚያው፥ እግረመንገዱን:: *ወደ ገበያ ሄጄ ወዲያው ዘመድ እጠይቃለሁ* ::

ወዳቂ "ወደቀ" ስር ተመ.

ወዳቃ ዝ.ክ.

ወዳድ "ወደደ" ስር ተመ.

ወዳጃ ስ አምልኮአዊነት ባለው ሁኔታ አዛውንት ሌሊት ሌሊት ጫት እየቃሙና ድቤ እየመቱ የሚያደርጉት ልመና፥ ፀሎት::

ወዳጅ "ወደደ" ስር ተመ.

ወደላ "ወደለ^{2}" ስር ተመ.

ወዴት ተው.ግ. አቅጣጫን፥ አድራሻን ለመጠየቅ የሚያገለግል ቃል:: *መስሪያ ቤትህ ወዴት ነው* ?

ወዴት ሄደ ተው.ግ. የት አለ፤ የት ጠፋ ::

ወጀብ ስ ከነፋስ ጋር ተቀላቅሎ አግድም የሚወረወር ዝናብ::

ወጀድ ስ በቤት ጓሮና አቅራቢያ የሆነ እርሻ፥ ቦታ (በአጥር፥ በቅጥር የተከበበ)::

ወጀ "ዋጀ" ስር **"ዋጀ"**ን ተመ.

ወገል ስ የቀለበት ቅርፅ ባለው ጫፉ በኩል ማረሻንና እርፍን ከድግር ጋር ባንድነት ጠርንቆ የሚይዝ፥ እንደ ሜንጦ ባለው ሌላው ጫፉ ደግሞ በወገል ጠፍር አማካይነት ከሞፈር ጋር የሚቆራኝ የማብርና እቃ(ለእሉን ሞፈር ስር ተመ.)::

ወገሜት(ወገሚት) ስ ተንጦ ቅቤው የወጣለት ወተት፤ አሬራ::

ወገረ ግ 1. በድንጋይ መታ፥ ደበደበ:: 2. ያዘ፥ አጠመደ (አሳን)::

ተወገረ ግ ተመታ፥ ተደበደበ::

ወገሬ ስ ነጭ የሆነ የማሽላ አይነት::

ወገርት ስ መድሃኒትነት አለው የሚባል አነስተኛ የሆነ የእፅዋት አይነት፤ ጪሱም ጥሩ ሽታ ስላለው በማእጠንትነት ያገለግላል::

ወገሸ ግ በጣም ተቆጣ፤ ሮጠ፥ በረረ፥ ፈረጠጠ፥ ደነበረ (ሰው፥ ከብት)::

ወገብ ስ 1. ከቂጥ በላይ ከትከሻ አካባቢ በታች ያለ የአካል ክፍል:: 2. ከዳሌ በላይ ከጎን በታች ያለ የአካል ክፍል:: *በሁለት እጆቹ ወገቡን ይዞ ቆሟል*:: 3. ዙሪያውን በቀበቶ ወይም በመቀነት የሚታሰረው የሰው አካላዊ ክፍል:: 4. ከፍታ ወይም ቁመት ላለው ነገር እንደ አማካይ የሚወሰድ ቦታ:: *ብርጭቆውን አትሙላው፤ እስከ ወገቡ ብቻ ቅዳልኝ*::

ወገቡ ቁምጥ አለ ሳያስበው፥ በድንገት ደነገጠ፥ ተስፋ ቆረጠ ::

ወገቡን ሞከረ ተፀዳዳ፥ እዳሪ ወጣ ::

ወገቡን ያዘው አስቸገረው፥ አስጨነቀው (ችግር) ::

ወገቤን አለ አነሰ፥ ቅቡጭ አለ፥ ሳይበቃ ቀረ (ገንዘብ፥...) ::

ወገበ ቀላል ቅ ሲሄድ፥ ሲራመድ ቀልጣፋ የሆነ፡ ፈጣን ።

ወገበ ነጭ ቅ ጠለቅ ያለ እውቀት የሌለው፡ ጥራዝ ነጠቅ ።

ወገብጌ ስ ጥብጣብ ወይም ቀበቶየሚያርፍበትና ወገብ ላይ የሚውለው የሱሪ የላይ ጫፍ ።

ወገነ ግ ወገን፡ ተባባሪ፡ አጋዥ ሆነ። *ከጠላት ጋር ወግኖ ወጋኝ።*

ወገን ስ 1. ዘመድ፡ ጓደኛ፡ በትውልድ፡ በብሄር፥ በዜግነት አንድ የሆነ። 2. አቅጣጫ፡ አኳያ፥ በኩል፥ ክፍል። *በዚህ ወገን በጎቹ ይበሉ፥ በሌላኛው ወገን ላሞቹን እናሰማራለን* ።

ወገን ለየ በዘር፡ በጎሳ፡ በነገድ ከፋፈለ ወይም ተከፋፈለ፡ በየፊናው፥ በየቡድኑ ሆነ። 2.ለዘመድ፥ ለወዳጅ አደላ ።

ወገን አደረገ ግ አጋር፥ ዘመድ፥ ጓደኛ አደረገ።

ባለወገን ቅ ደጋፊ፥ አጋዥ ያለው።

የወገን ቅፅል ስ ዝምድናን፡ ወገንነትን የሚያሳይ ቅፅል (ዊ)። *ኢትዮጵያዊ*፡

የወገን ጦር ስ የራስ የሆነ ጦር ።

ወገኛ "*ወጋ" ስር ተመ.

*ወገዘ

ውጉዝ ቅ (ሃይ.) የተወገዘ፡ የተከለከለ፡ መጥፎ የተባለ።

ውግዘት ስ 1. ግዝት። 2. መነቀፍ፥ መረገም (በመጥፎ ድርጊት፥ ሁኔታ ምክንያት) ።

ተወገዘ ግ 1. ከሃይማኖት ማህበር እንዲወጣ፥ እንዲለይ፥ እንዲገለል ተደረገ ፥ተገዘተ። 2. ተወቀሰ፥ ተነቀፈ፥ መጥፎ ተባለ ። 3.መጥፎ በመሆኑ በሰው ተረገመ፡ ተከለከለ።

አወገዘ ግ 1. ከሃይማኖት ማህበር አስወጣ፥ ለየ፡ ረገመ። 2. ተቃወመ፥ ነቀፈ፥ አጥላላ።

ወገዝ ስ ከጥጃ በላይ ከወይፈን ወይም ከጊደር በታች የሆነና ጡት የተወ ከብት ።

*ወገደ

ወግድ(ወጊድ፥ ወይድ) ግ ራቅ፥ ዞር በል፡ ከፊቴ ሂድ የሚል ትእዛዛዊ የቁጣ ቃል ።

ተወገደ ግ 1. ራቀ፥ እንዳይደርስ ተከለከለ፡ ተለየ። 2. ጠፋ፡ ተቃለለ። *ችግሩ ተወገደ* ።

አስወገደ ግ 1. አራቀ፡ አገለለ። 2. አጠፋ፡ እንዳይኖር አደረገ፥ አቃለለ (ችግርን፥...)።

ወገግ

ውጋገን(ውጋጋን) ስ ከርቀት የሚታይ የፀሃይ፡ የጨረቃ፡ የእሳት ፡... ብርሃን።

ወገግታ ስ የንጋት ብርሃን።

ወገግ አለ ግ ብርሃን ፈነጠቀ፡ ታየ፡ ጨለማ የነበረው ብርሃን እየሆነ መጣ።

ወገጠ "ወቀጠ" ን ተመ.

ወጊድ "*ወገደ" ስር ተመ.

ወጋ ግ 1. በመርፌ፥ በጦር፥ በሳንጃ ወይም በሌላ ሹል ነገር አንድን አካል ጠቅ አደረገ፥ ሸቀሸቀ። 2. (ዘይ.) ክፉ ነገርን ተናገረ፥ አሸሟጠጠ። *በነገር ወጋኝ*። 3. ውጋት አመመ (ጎንን፡ ጀርባን፥...)። 4. በውጋ የገበጣ ጨዋታ ጊዜ የጠጠር አሿሪው (የተጫዋቹ) የመጨረሻ ጠጠር ሶስት ጠጠር በያዘ ጉድጓድ ውስጥ አረፈ፡ ጉድጓዱም የተጫዋቹ ውጋ ሆነ። 5. አይን ላይ የህመም ስሜት ፈጠረ፥ አይንን አስጨፈነ (ጨረር፥ ሃይለኛ የብርሃን ነፀብራቅ)። 6. በጦር ሃይል አጠቃ፡ ጉዳት አደረሰ። 7. ለተመ፥ ገጨ፥ በሳ (በሬ፡ በግ፥... በግንባር፥ በቀንድ፥...)።

ውጊያ ስ ጦርነት፥ ፍልሚያ።

ውጋት ስ 1. ጠቅ የሚያደርግ፡ ቀስፎ የሚይዝ የህመም አይነት። ቅ 2. (ዘይ.) ጨቅጫቃ፥ ነዝናዛ።

ውጋ ስ በውጋ የገበጣ ጨዋታ ላይ አንድ ተጫዋች ጠጠር በሚያዞርበት ጊዜ እጁ ላይ የምትቀረዋ የመጨረሻዋ ጠጠር የምታርፍበት ሶስት ጠጠር የያዘች ጉድጓድ፥ ያቺም ጉድጓድ የተጫዋቹ ውጋ ትሆናለች።

ተወጋ ግ 1. በመርፌ፥ በጦር፥ በሳንጃ ወይም በሌላ ሹል ነገር ጠቅ ተደረገ፥ ተሸቀሸቀ። 2. ተጠምዶ ተያዘ (በጥላቻ)።

ተዋጋ ግ 1. ጦር፥ ጠመንጃ፥... በመያዝ በጦር ሜዳ ተፋለመ። 2.ታገለ (በሙግት፥በክርክር፥...)። 3. ተላተመ፥ ተፋለመ (ከብት)።

ተዋጊ ቅ 1. በውጊያ ላይ ያለ ወይም ለውጊያ የተዘጋጀ ሃይል ወይም ሰው። 2. ላመለኛ፥ አስቸጋሪ የሆነና የሚዋጋ ከብት።

አዋጋ ግ 1. በጦር ሜዳ ላይ ተዋጊዎቹን በማዘዝና በመምራት አፋለመ ። 2. በጦርነት ለመፋለም ምክንያት ሆነ። 3. (ዘይ.) ክፉ ነገርን፡ ወሬን ከአንዱ ሰው ወደ ሌላው በማስተላለፍ አጣላ።

አዋጊ ስ 1. በጦርነት ላይ የሚያፋልም የወታደሮች መሪ። ቅ 2. ነገር እያሳበቀ የሚያጣላ።

አስወጋ ግ እንዲጠመድ አደረገ (በነገር)።

*ወጋ

ወግ ስ 1. ስርአት፡ ደንብ (ከጥንት ሲያያዝ የመጣ)። 2. ወሬ፥ ነገር፥ ጭውውት።

ለወግ ለማእረግ ደረሰ ትዳር፡ ሹመት፥...ለመያዝ፥ ለማግኘት በቃ ።

ወግ ወጉን ይዞታል የተሳካም ባይሆን ለማስመሰል ሞክሯል (አንድን ነገር በማድረግ) ::

ወግ ደረሰው 1. ክብር አገኘ፥ የደንቡ ተሟላለት። 2. ሌሎች የሚያደርጉትን ነገር ለመጀመሪያ ጊዜ አደረገ። *ለቶሎሳ ወግ ደርሶት በግ አረደ።*

በወግ በወጉ በመልክ በመልኩ ወይም ስነስርአት ባለው መንገድ ::

ወግ ጠርቅ ቅ 1. ወሬኛ፥ ተናግሮ የማያባራ። 2. ወገኛ፥ ወሬ ወዳድ።

ወግ አጥባቂ ቅ የጥንትን ወግ፥ ባህል እንዳለ እንዲቆይ፥ እንዳይሻሻል፥ እንዳይለወጥ የሚሻ (ሰው፥ ድርጅት፥...) ::

የወግ እቃ ስ ባህላዊ የሆነ የሽልማት፥ የጌጣጌጥ፥ የክብር፥...እቃ ::

ወገኛ ቅ 1. ወግን፥ የቆየ ደንብን አጥባቂ። 2. (ስድብ) ጉረኛ ከሆነው በላይ ለመምሰል ፈላጊ።

አወጋ ግ አወራ፥ ተጫወተ።

ወጋግራ ስ የቤት ጣሪያን እንደምሰሶ ደግፎ በመያዝ የሚያገለግል ወፍራም እንጨት።

ወጌሻ ስ ወለምታን፥ ስብራትን ፥ ውልቃትን በማሸት፥ በመጠገን የሚያክም የልምድ ወይም ስልጠና ያለው ባለሙያ።

ወግ "*ወጋ" ስር ተመ.

ወግድ "*ወገደ" ስር ተመ.

ወጠምሻ ስ እድሜው ያልገፋ፥ ደንዳና፥ ወፍራም፥ ጉልበታም ሰው።

ወጠረ ግ 1. ስቦ ያዘ፥ ለጠጠ (የአልጋ ሽቦን፥ ብራናን፥ ቆዳን፥...)። 2. ሆድን ነፋ፥ ቀበተተ። *የበላሁት ምግብ ሆዴን ወጥሮታል።* 3. መጣሁ መጣሁ አለ፥ አስጨነቀ (ሽንት፥ አይነምድር)። 4. አፋጦ ያዘ፥ ሠረመረ። *በጥያቄ ወጥሮ ያዘው።* 5. ትእቢት ያዘ፥ ኩራት ኩራት አለው። *ምን ይወጥረዋል?* 6. ጠበበ፥ በደንብ አልገባ አለ (ልብስ)። 7. መንገዱ ለጠላት እንዳያመች በወታደራዊ ስልት ጠበቀ። *ከንጉሡ ሊያልፍ ነውና ከድልድዩ እስከ ከተማው ያለው መንገድ ይወጠር።*

መወጠሪያ ስ 1. ከእንጨት የተሰራ የቆዳ፥ የብራና መገተሪያ። 2. በልብስ ስፌት መኪና አማካይነት ጨርቅ ላይ ጥልፍ ለመጥለፍ የሚያስችል ከእንጨት ወይም ከሌላ ነገር የሚሰራና ጨርቁን ወጥሮ የሚይዝ ክብ እቃ።

ውጥረት ስ ጭንቀት፥ ጥበት (በስራ ብዛት፥ በጠርነት፥...)።

ውጥር ውጥር አለ ግ በኩራት መንፈስ ቀንን ቀንን አለ፥ ቀንጥር ቀንጥር አለ፥ ያላቅሙ ተንጠራራ።

ተወጠረ ግ 1. ተስቦ ተያዘ፥ በሃይል ተዘረጋ፥ ተገተረ፥ ተለጠጠ። 2. ተያዘ፥ ተጨነቀ (በችግር፥ በፈተና፥...)። 3. በትእቢት ተሞላ፥ ታበየ። 4. ቁዝር አለ፥ ተነፋ፥ ተቀበተተ (ለምሳሌ ሆድ)።

ተወጣጠረ ግ አለቅጥ ኮራ፥ ትእቢት ያዘው።

ወጠቀ ግ በብዛት በላ፥ ጠቀጠቀ ::

ወጠነ ግ 1. ጀመረ፥ መሰረት ጣለ። 2. አቀደ።

ውጥን ቅ ጅምር፥ እቅድ።

ተወጠነ ግ ተጀመረ፥ ታቀደ።

ተውጠነጠነ ግ ታሰበ፥ ታቀደ፥ (አንድን ድርጊት ለመፈፀም፥ ለመስራት) ::

አውጠነጠነ ግ አሰበ፥ አሰላሰለ፥ አወጣ አወረደ፥ አቀደ (ሃሳብን) ::

ወጠጤ ስ 1. ለመጥቃት የደረሰ ወንድ በግ፥ ፍየል። ቅ 2. (ስድብ) ያልሰከነ፥ ያልበሰለ፥ ውረጋጥ ::

ወጣ ግ 1. ከውስጥ ወደ ውጭ ሄደ። 2 ከታች ወደላይ፥ ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ ቦታ ተንቀሳቀሰ፥ ተረማመደ። 3. አለ፥ ተናገረ። *ከቃል ወጣው።* 4. ተለየ፥ ተወገደ። *ከቤት ከወጣ ብዙ ጊዜው ነው።* 5. በቀለ፥ አደገ፥ ረዘመ። 6. ጨረሰ፥ ዘለቀ፥ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ደረሰ። *መፅሃፉን ወጣው።* 7. ይፋ ሆነ፥ ተነገረ፥ ተገለፀ። *ምስጢሩ ወጣ።* 8. ታየ፥ ብቅ አለ። *ፀሃይ ወጣች።* 9. ደረሰ፥ የባለ እድሉ ስም፥ ቁጥር ተመረጠ (ሎተሪ ወይም እጣ)። 10. ወጪ ተደረገ። 11. በስብሰባ፥ በሰልፍ ላይ ተገኘ። *ለሰልፉ ብዙ ሰው ወጣ።* 12. ተነቀለ፥ ተወገደ። *ጥርሱ ወጣለት።* 13. በቀለ፥ ተፈጠረ። *ብጉር ወጣበት።* 14. ለቀቀ። *እድፉ ወጣ።* 15. ለህዝብ ቀረበ። *መፅሄቱ ታትሞ ወጣ።* 16. የ__ ማእረግ፥ ደረጃ ያዘ ወይም አገኘ። *በፈተና አንደኛ ወጣ።*

ወጣ አለ ግ 1. ለትንሽ ጊዜ ከቤት ወይም ከሃገር ውጭ ሄደ። 2. ለየት አለ፥ አፈነገጠ ::

ወጣለት 1. ረካ (የፈለገውን ተናግሮ፥ በልቶ፥ አድርጎ፥...)። 2. ዳነ፥ ሻረ። *ሱፍጁ ወጣለት።*

ወጣው 1. ሆነ። *ጥሩ ሃኪም ወጣው።* 2. ተናገረ። *የልመጣኝን ተናገረ ሳትበለ።* 3. አጠፋ፥ ከፈለ (ገንዘብን)። *ዛሬ ገና ገንዘብ ወጣው።*

በ__ ወጣ __ን መስሎ ተወለደ፥ ባህርዩን ወረሰ፥ አደገ። *በአባቱ ወጣ።*

በወጣ ያውጣው (እንዳወጣ ያውጣው) እንደሆነ ይሁን።

የወጣለት ደንበኛ፥ አይነተኛ፥ የታወቀ። *የወጣለት ሰካራም ነው።*

የወጣለት ስራ የተሳካ ስራ፥ ጥሩ ሆኖ የተሰራ።

ወጣ ገባ ቅ ያልተስተካከለ፡ አባጣ ጎባጣ ።

ውጣ ውረድ ስ ድካም፡ ልፋት ።

መውጫ ስ 1. ከውስጥ ወደ ውጭ፡ ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ ቦታ መተላለፊያ ወይም መሹለኪያ (በር፥ መሰላል፥...)። 2. መፍትሄ። *ለችግሩ መውጫ ጠፋ*። 3. ብቅ የሚባልበት፡ የሚታይበት ጊዜ፥ አቅጣጫ። *በፀሀይ መውጫ በኩል* ።

መውጫ መግቢያ አጣ ተቸገረ፥ ተጨነቀ፡ ሲወጣ ሲገባ ችግር ገጠመው ።

መውጫ መግቢያውን ያውቃል የቤቱን፥ የቦታውን፥... ሁኔታ ጠንቅቆ ያውቃል።

መውጫ ቀዳዳ አጣ ከችግር፥ ከጭንቅ የሚላቀቅበት ዘዴ አጣ ።

ወጥ ቅ 1. ሙሉውን በአንድ አይነት መልክ የተሰራ፥ አንድ አይነት የሆነ። 2. አዲስ፥ ያልተቀዳ፥ ያልተኮረጀ (ሃሳብ፡ ድርሰት፥...)።

ወጪ(ወጭ) ስ ለልዩ ልዩ ጉዳይ የተከፈለ ወይም ለስራ፥ ለኑሮ የሚያስፈልግ ገንዘብ ።

ወጪ አደረገ ለተለያየ ጉዳይ፡ ለስራ፥...ገንዘብ ከፈለ።

ወጪውን ሸፈነ ለስራ፡ ለኑሮ፥ ለድግስ፥... የሚያስፈልገውን ገንዘብ ሰጠ፥ ከፈለ፥ ቻለ ።

ወጪና ገቢ ስ የተከፈለና የተሰበሰበ ገንዘብ ።

የወጪ አንድ ሰው ወደ ሌላ ቦታ በሚሄድበት ጊዜ የሚደረግ የመሰነባበቻ ግብዣ ።

የወጪ ሰነድ ስ ገንዘብ ለተወሰነ ጉዳይ መከፈሉን የሚያረጋግጥ ማስረጃ፡ ደረሰኝ ።

ውጤት ስ 1. አንድን ምክንያት ወይም ድርጊት ተከትሎ የመጣ፥ የታየ ሁኔታ ወይም ነገር። 2. ጥሩ ነገር፥ ፍሬ። *ድካምህ ከንቱ አይቀርም፥ ውጤት ይኖረዋል*። 3. በፈተና ወይም በውድድር፥... የተደረሰበት፡ የተገኘ ነጥብ። 4. በመደመር፡ በማባዛት፥... የተደረሰበት የሂሳብ፡ የስሌት መልስ፤ በምርምራ፥ በሙከራ የታወቀ ግኝት። 5. ፍሬ፥ ሰብል፥ ምርት። 6. ትርፍ፥ ጥቅም። *ንግዱ ውጤት የለውም*።

ውጤት አመጣ በፈተና፥ በውድድር፥ በስራ ነጥብ ወይም ጥቅም አገኘ።

ውጭ(ውጪ) ተው.ግ. 1. ደጅ። 2. ከአንድ ክልል፥ ድንበር፥ አጥር፥... ወዲያ። 3. በአንድ ደንብ፡ ስርአት፥ ህግ፥ ባህል፥... ውስጥ የሌለ ።

ውጭ አደረ ዘወትር በሚያድርበት ቤት ሳይሆን ሌላ ቦታ አደረ ።

በውጭ ሲያዩት ጠለቅ ሳይሉ፡ ላይ ላዩን ሲያዩት።

ውጭ ነፍስ ግቢ ነፍስ ጭንቅ፥ ጣር ።

ውጭ [አገር] ስ ባህር ማዶ፡ በሌላ መንግስት የሚመራ ሃገር ።

ውጭ ጉዳይ ስ በሃገሮች መካከል ያለውን ግንኙነት የሚመለከት ጉዳይ ።

የውጭ ንግድ ስ ከሌላ ሃገር ጋር የሚደረግ ንግድ ።

የውጭ ምንዛሪ ስ የሌላ ሃገር ገንዘብ፡ ዶላር፥ ፓውንድ፥...።

የውጭው አለም ስ 1. ሌሎች አገሮች። 2. አካባቢ። *በስሜት ህዋሳታችን አማካይነት ስለውጭው አለም እናውቃለን*።

ተወጣ ግ ተግባሩን፡ ግዳጁን፥ ችግሩን አቀለለ፡ ጨረሰ፥ ፈፀመ።

መወጣጫ ስ መሸጋገሪያ፥ እርካብ፥ መሰላል።

ተዋጣ ግ 1. ገንዘብ ለእርዳታ ወይም ለሌላ ጉዳይ ተሰበሰበ። 2. አማረ፥ ተሳካ፥ ሰመረ።

መዋጮ ስ ከተለያዩ ግለሰቦች፥ ቡድኖች፥... የተዋጣ፡ የተሰበሰበ ገንዘብ።

ተውጣጣ ግ 1. ከተለያየ ወገን፥ አካባቢ ወይም ቡድን፥... ተሰባሰበ (ሰው፥ ሃሳብ፥...)። 2. የተለያየ ዘዴን በመጠቀም ሊደረስበትና ሊታወቅ ቻለ፡ ይፋ ሆነ፡ ታወቀ (ምስጢሩ) ።

አወጣ ግ 1. ከውስጥ ወደ ውጭ ወሰደ፡ አጓዘ። 2. ከፈለ፥ ወጪ አደረገ፡ አጠፋ (ገንዘብን)። 3. ወሰደ፥ ወጪ አደረገ (ገንዘብን ከባንክ)። 4. አበጀ፥ ሰራ፥ ፈጠረ። *መንገድ አወጣ/ስልት አወጣ*፡ 5. ፈለፈለ፡ አገኘ (ማእድንን፥ ወይም ሌላ የተደበቀ ነገርን፥...)። 6. ተሸጠ፥ አስገኘ። *መፅሃፉ አስር ብር አወጣ*፡ 7. አስነገረ፥ ለህዝብ አቀረበ፥ አሰማ። *አዋጅ አወጣ/ማስታወቂያ አወጣ*፡ 8. አበቀለ። *ጥርስ አወጣ/ሽበት አወጣ*፡ 9. ይፋ፥ ግልፅ አደረገ (ምስጢርን፥...)። 10. አተረፈ፡ አዳነ። *ከገደል አወጣች*፡ 11. ደነገገ። *ህግ አወጣ* ። 12. ነደፈ፥ ቀየሰ። *ፕላን አወጣ*፡

አወጣ አወረደ አሰበ፥ አሰላሰለ ።

አውጭ ስ እሬሳ እያወጣ የሚበላ አውሬ ።

ማውጫ ስ 1. በየመፅሃፉ፥... የመጀመሪያ ገፆች አካባቢ ተሰፍሮ የሚገኝ፡ በመፅሃፉ ውስጥ ያሉትን ንኡሳን ርእሶች ወይም አርእስተ ነገሮችና መገኛቸውን ገፅ የሚመለከት ዝርዝር። 2. በሎተሪ አሸናፊ የሆኑትን እጣዎች ዝርዝር የያዘ ሰንጠረዥ።

አዋጣ ግ 1. የሚደርስበትን ወይም የሚችለውን ያህል ገንዘብ ወይም ሌላ ነገር ሰጠ (ለችግር፥ ለደስታ፥ ለግብዣ፥...የሚሆን)። 2. ትርፍ አስገኘ። *ሸቀጡን በሰላሳ ብር ብሸጠው ያዋጣኛል*። 3. አዛለቀ። *ሁልጊዜ መዝናናት አያዋጣም*።

አውጣጣ ግ 1. ደብቆ የያዘውን ምስጢር ወይም ጉዳይ (የተለያየ ዘዴ በመጠቀም) እንዲናገር ገፋፋ፥ አስለፈለፈ። 2. ከተለያየ ቦታ አሰባሰበ (ሰዎችን፡ ገንዘብን)።

አውጫጭኝ ስ በስውር ከብት ሲሰረቅ፣ ሰው ሞቶ ሲገኝ ወይም የተለያየ ወንጀል ሲፈፀም የአካባቢው ሰው ተሰብስቦ ወንጀለኛውን ለመጠቆም የሚጠቀምበት ዘዴ፤ አፈርሳታ ።

ወጣት ስ 1 እድሜው ከአስራ ስምንት እስከ ሰላሳ አመት የሚሆን ሰው። 2 ጠንካራ፣ ብርቱ፣ ያላረጀ። *አባቱ ገና ወጣት ናቸው።* 3 አዲስ፣ ያልደረጀ፣ ያልዳበረ።

ወጣጠረ "ወጠረ" ስር ተመ.

ወጥ ስ ሽሮ ወይም ክክ ወይም አትክልት ወይም ስጋ፣... በዘይት ወይም በቅቤ ከተቁላላ ሽንኩርት፣ በርበሬ ወይም እርድ እንዲሁም ከውሃ ጋር አዋህዶ በማብሰል የሚዘጋጅ የእንጀራ ማባያ።

ወጥ ረገጠ ባለገ፤ ገደብ አለፈ፤ ስርአት የለሽ ሆነ (ታላቁን፣ መከበር ያለበትን ባለማክበሩ፣...)።

ወጥ ሰራ ወጥን አዘጋጀ፤ አበሰለ።

ወጥ አወጣ ውጥን በጭልፋ እየጨለፈ ከሰሃን ወይም ከእንጀራ ላይ አደረገ።

ወጥ ቤት ስ 1. መደበኛ ስራው ወጥ መስራት የሆነ ሰራተኛ። 2. በድግስ ወይም በግብዣ ጊዜ ወጥ ለማሳለፍ የተመደበ ሰው። 3. ወጥ የሚዘጋጅበት ቤት፤ ኩሽና ።

የወጥ ቤት እቃ ስ ድስት፣ ሰሃን፣ ጭልፋ፣...የመሳሰሉት የምግብ ቤት እቃዎች።

ወጥ "ወጣ" ስር ተመ.

ወጥመድ ስ 1. አውሬን ለመያዝ ወይም ለመግደል የሚያገለግል መሳሪያ። 2. አንድን ሰው ለመጉዳት የተቀናበረ ወይም የተዘጋጀ ተንኮል፣ ሴራ፣...።

ወጥመዱ ያዘለት ለመጉዳት ያዘጋጀው ሴራ፣ ተንኮል ተሳካለት።

ወጥመድ ውስጥ ገባ የሴራ የተንኮል፣... ሰለባ ሆነ።

ወጨፎ^1 ስ ከነፋስ ጋር እየተቀሳቀሰ አግድም የሚዘንብ ዝናብ፤ ውሽንፍር።

ወጨፎ^2 ስ ጥንት የነበረ የጠመንጃ አይነት ።

ወጪ "ወጣ" ስር ተመ.

ወጭ "ወጣ" ስር **"ወጪ"**ን ተመ.

ወጭማፃ ቅ 1. (ስድብ) ሰባራ፣ ሰንካላ። 2. አቅመ ቢስ፣ ተልካሻ ።

ወጭት ስ ከሸክላ ወይም ከነሃስ ወይም ከብረት የሚሰራ የወጥ ቤት እቃ ።

ወጭት ሰባሪ ውለታ ቢስ።

ወጭት አብሽ ስ ከባቄላና ከአብሽ የሚሰራ፣ ከሌላ ወጥ በፊት የሚቀርብ ማባያ።

ወፈረ ግ 1 አካል ጨመረ፣ ደነደነ፣ ሰባ፣ ግዙፍ ሆነ። 2. ለደለደ፣ የውሃው መጠን አነስ ያለ ሆነ (ወጥ፣ ቡና፣...)።

ወፍራም ቅ 1. ጠብደል፣ ደንዳና፣ ግዙፍ። 2. ቀጭን ያልሆነ (ለምሳሌ ወጥ፣ ቡና፣...)።

ወፍራም ቆዳ አለው ችግር፣ መከራ ይችላል ወይም ይቋቋማል።

ወፍራም ደመወዝ ትልቅ ደመወዝ።

ውፍረት(ውፋሬ) ስ 1. የሰውነት ድንዳኔ። 2. የአንድ አካል የመጻነስ መጠን፤ ግዝፈት ።

አወፈረ ግ ወፍራም አደረገ።

ወፈፈ ግ አበደ፤ አእምሮውን ሳተ።

ወፈፍ አደረገ ግ አሳበደ፣ አእምሮን አሳተ ።

ወፈፌ ቅ እብድ፤ ቀዥቃዣ ።

ወፈፍተኛ ቅ 1. በድንገት የሚቆጣ፣ ግልፍተኛ። 2. እብድነት ያለበት፣ አእምሮው የተነካ ።

ወፍ(ብ.ቁ. **ወፎች፣ አእዋፍ**) ስ 1. ሁለት እግርና ሁለት ክንፍ ያለው፣ አየር እየቀዘፈ መብረር የሚችል፣ አካሉ በላባ የተሸፈነ እንስሳ (ስእሉን በሚቀጥለው ገፅ ተመ.)። 2. በአንድ ጫፉ ሰረገላ ላይ የሚቆም በሌላው ጫፉ ወራጅ የሚሸከም፣ ጣሪያ ለማዋቀር የሚያገለግል በወፍ ቅርፅ የሚዘጋጅ እንጨት። 3. አውጫጭኝ ወይም አፈርሳታ በሚካሄድበት ጊዜ ወንጀለኛውን ለሚጠቁም ሰው የሚሰጠው የድብቅ ስም።

ወፌ ቆመች በእግሩ ለመቆም የሚሞክርን ህፃን ለማበረታታት የሚባል አነጋገር ።

ወፈ ያሬድ ስ ድምፀ መልካም የሆነ የወፍ አይነት።

ወፈ ገነት "ጣዎስ" ን ተመ.

ወፈ ግዝት ቅ ግዝት አስፈላጊነት ሳይኖረው ወይም ባለማወቅ አግባብነት በሌለው ጉዳይ ላይ ሁሉ የግዝት ቃል የሚያስተላልፍ ።

ወፍ ሲንጫጫ በጧት፣ በማለዳ ።

ወፍ አርግፍ ስ ቡዳ፤ ጠይብ ።

ወፍ አእላፍ ቅ እጅግ በጣም ብዙ የሆነ (ሰው ወይም የወፍ መንጋ) ።

ወፍ እግር ስ 1. በእጅ መርፌ የሚሰፋ፣ ጫፍና ጫፉ የወፍ እግር የሚመስል ጥልፍልፍ የሆነ የነጠላ ልብሶች አሰፋፍ። 2. (ስድብ) ቀጭን እግር።

ወፍ ዘረር "ዘረር" ን ተመ.

ወፍዘራሽ ስ 1. ሰው ሳይተክለው በዱር የበቀለ ተክል፤ ወፍ እራሽም ይባላል። ቅ 2. በጥሩ ስነምግባር ያላደገ፣ ባለጌ።

የወፍ ቆሎ ስ ስሩ ሲበሉት የሚጣፍጥ የእንግጫ አይነት።



1. ጣዎስ
2. በቀቀን
3. ጨሰቁ
4. ንበበል

5. ግንደ ቆርቁር
6. የሌሊት ወፍ
7. ቆቅ
8. ድንቢጥ

9. ጭሩ
10. ጭሪ
11. የረግረግ ወፍ
12. ሰጎን

13. ዋኔ
14. ርግብ

የወፍ ቋንቋ ስ ለብዙዎች ግልፅ ያልሆነ፣ ጥቂት ሰዎች ፈጥረው የሚገለገሉበት ምስጢራዊ ቋንቋ ።

የወፍ በሽታ ስ አይንን፣ ጥፍርን፣ ሽንትን ቢጫ የሚያስመስል የጉበት በሽታ ።

የወፍ ጎጆ ስ ወፎች ከሳር፣ ከገለባ፣ ከላባ፣...የሚሰሩት ማደሪያ፣ እንቁላል መጣያና መኖሪያ ።

ወፍራም "ወፈረ" ስር ተመ.

ወፍቾ ስ የደረቀ የእንሰት ቅርፊት ።

ወፍጮ ስ በሰው ጉልበት ወይም በሞተር ኃይል ሊሰራ የሚችልና እህልን ወይም ሌላ ነገርን ለመፍጨት፣ ለማድቀቅ የሚያገለግል እቃ፣ መሳሪያ፣ ወይም የተወቀረ ድንጋይ።



ወፍጮ መድፊያ ስ ከሆሳእና ዋዜማ በፊት ያለው አርብ ቀን፣ እህል የማይፈጭበት ።

ወፍጮ ቤት ስ የሞተር ወፍጮ የተተከለበትና አገልግሎት የሚሰጥበት ቤት ።

የወፍጮ ልጅ ስ የወፍጮ መጅ ።

የወፍጮ እህል ስ ሲፈጭ የተዘጋጀ እህል ።

ዉ የ"ወ" ፊደል ካእብ ዘር ።

ዊ የ"ወ" ፊደል ሳልስ ዘር ።

-ዊ (-አዊ) 1. ከተፀውኦ ስሞች በስተመጨረሻ እየገባ ወገንነትን የሚገልፅ ምእላድ፣ የወገን ቅፅል። *ኢትዮጵያዊ*፡ 2. በ ___ በኩል፣ የ___ የሚል ትርጉም የሚሰጥ ምእላድ። *ሰማያዊ /ውጫዊ/ሃይማኖታዊ/ ወቅታዊ* ።

ዋ¹ የ"ወ" ፊደል ራብእ ዘር ።

ዋ² የማስጠንቀቂያ፣ የማስፈራሪያ፣ የዛቻ መግለጫ። *ዋ! ተሳስተህ ታበላሽና ትቀጣለህ* ።

ዋ³ የሃዘን፣ የትካዜ መግለጫ። *ዋ! ያን የመሰለ ጀግና ተበላሸ* ።

-ዋ¹ የሶስተኛ መደብ አንስታይ ፆታን የሚያመለክት መስተአምር። *አንበሳዋ* ።

-ዋ² የሶስተኛ መደብ አንስታይ ፆታ አገናዛቢ ምእላድ። *ቦርሳዋ ተከፍቷል*።

ዋ³ "ሆይ" እንደማለት የሚያገለግል ቃለ አጋኖ። *ላንቺዬዋ/ልጄዋ*።

***ዋሃደ**

ውህደት ስ አንድ መሆን፣ መቀላቀል ።

ተዋሃደ ግ አንድ ሆነ፣ ተቀላቀለ ።

ተዋህዶ ስ መለኮትና ትስብእት ተዋህደው አንድ አካል፣ አንድ ባህርይ፣ አንድ ፈቃድ ሆኑ የሚል ሃይማኖታዊ አስተምህሮ ።

አዋሃደ ግ አንድ አደረገ፣ አቀላቀለ ።

ዋለ¹ ግ 1. ሙሉውን ቀን ወይም ከቀኑ አብዛኛውን ክፍል በአንድ ቦታ ቆየ፣ ብዙ ጊዜ አሳለፈ። 2. ስራ ተሰራበት፣ አገልግሎት ሰጠ። *ገንዘቡ ስራ ላይ ዋለ* ። 3. በአንድ በተወሰነ ቀን ላይ ሆነ፣ አረፈ። *እንቁጣጣሽ እሁድ እለት ዋለ*።

ዋለ አደረ ሰነበተ፣ ለተወሰኑ ቀናት ቆየ።

ሳይውል ሳያድር ዛሬውኑ ።

በዋል ፈሰስ በሄደበት የሚቆይ፣ ቶሎ የማይመለስ፣ ግዴለሽ ።

ውሎ አደረ ቆየ፣ ሰነበተ ።

ውሎ ገባ(ውሎ ገብ) ቅ በዕለት ሄደው ሳያድሩ የሚመለሱበት የደርሶ መልስ መንገድ፣ ጉዞ። *መንገዱ የውሎ ገብ መንገድ ነው* ።

ውሎ ይግባ (ምር.) በሰላም፣ በጤና ይኑር፣ በሰላም ውሎ በሰላም ይመለስ ።

እየዋለ እያደረ እየቆየ፣ እየሰነበተ ።

የዋለ ቅ የቆየ፣ ትኩስ ያልሆነ። *የዋለ እንጀራ*።

መዋያ ስ ቀኑን፣ ጊዜውን ማሳለፊያ ቦታ።

ውሎ ስ 1. የሙሉ ወይም የግማሽ ቀን ቆይታ። 2. ሬሳው በሌሊት ዘመድ ወዳጅ ተሰብስቦና አልቃሽ ቆሞ ቀኑን ሙሉ ለሞተው ሰው የሚደረግ ልቅሶ ።

ውሎ ተዋለ ሲለቀስ ዋለ።

የውሎ አበል ስ ለስራ ጉዳይ ከመስሪያ ቤቱ ርቆ ለሚሄድ ደመወዝተኛ በቀን ሂሳብ የሚከፈል ገንዘብ።

አዋለ ግ 1. አቆየ። 2. አንድ ስራ እንዲሰራበት፣ እንዲካሄድበት አደረገ (ገንዘብን፣ ጉልበትን)። *ገንዘቡን ንግድ ላይ አዋለ*።

አዋይ ስ የቤት ውስጥ ቆሌ።

የአዋይ አዋይ ትፈልገዋለች በሚል ልማዳዊ እምነት መሶብ ውስጥ የሚቀመጥ ቁራሽ እንጀራ።

የአዋይ በላ ቅ ለአዋይ የሚቀመጠውን ቁራሽ እንኳ የሚበላ ችጋራም፣ ስግብግብ፣ ረሃብ የማይችል።

ዋለ² ግ 1. በጎ ስራ ሰራ፣ ውለታ አደረገ። 2. ረዳ፣ አገዘ፣ አዳነ። *ዛሬ እግዜር ዋለልኝ* ።

ውል ስ 1. ስምምነት፣ ለመስራት፣ ለመፈፀም የተገባ ቃል፣ ውለታ። 2. የቋጠሮ መፍቻ ምልክት።

ውል ሰረዘ በውሉ መሰረት ማከናወን ማቆሙን

አሳወቀ፤ ውሉን አፈረሰ።

ውል አፈረሰ በተዋዋለውና በተስማማው መሰረት ማከናወኑን ተወ፤ ስምምነቱን ጣሰ ።

ውል ገባ(አደረገ) ተዋዋለ፤ ተስማማ ።

ውሉ ጠፋ ተምታታ፤ መፍትሄ አፈላለጉ አስቸጋሪ ሆነ።

ውል ሰሚ ስ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች ወይም ድርጅቶች ሲዋዋሉ በአማኝነት፣ በምስክርነት የሚያዳምጥ ።

ውል ሰጪ ስ በውል ስምምነት ድርድር ላይ ስራው እንዲሰራለት፣ ጉዳዩ እንዲፈፀምለት የሚጠይቀው ወይም ቃል የሚያስገባው ወገን (ለምሳሌ በህንፃ ስራ ውል ውስጥ አሰሪው ውል ሰጪ ነው)።

ውል ተቀባይ ስ አንድን ተግባር ለማከናወን፤ ለመስራት ከግለሰብ፤ ከድርጅት ጋር ውል የገባ ወገን።

ውል የለሽ ቅ 1. በቃሉ የማይገኝ፤ ቀልማዳ። 2. የተወሳሰበ፤ የተሳሰረ፤ የተምታታ ።

ውል ያለው ነገር መልክ ያለው፣ መሰረት ያለው ነገር፤ ቁም ነገር ።

ውለታ ስ 1. አንዱ ለሌላው የሚያደርገው በጎ ስራ፤ ቁም ነገር። 2. የ"**ውል**"ን 1ኛ ፍቺ ተመ.

ውለታ መለሰ ለተደረገለት በጎ ተግባር በፈንታው በጎ ነገር አደረገ፤ ብድር መለሰ ።

ባለውለታ በጎ ተግባር ያደረገ፣ ቁም ነገር የሰራ። *እገሌ ባለውለታዬ ነው።*

ውለታ ቢስ ቅ የተደረገለትን ውለታ የሚዘነጋ፣ ምስጋና ቢስ ።

ውለኛ ቅ ቁምነገረኛ፤ በተናገረበት፣ ባለበት የሚገኝ ።

ተዋዋለ ግ ተስማማ፤ ውል ገባ፣ የውል ስምምነት ፈፀመ።

አዋዋለ ግ አስማማ (በስራ፤ በገንዘብ) ።

አዋዋይ ስ ውል የሚያፈራርም፤ የሚያስማማ አካል ።

ዋለለ ግ 1. ዋዠቀ፣ ተንቃነቀ፣ ወዲያና ወዲህ አለ። 2. ባከነ፣ እርጋታ አጣ። 3. መወሰን አቃተው።

አዋለለ ግ 1. እንዲዋልል አደረገ፤ አንቃነቀ፤ አዋዠቀ። 2. አባከነ፣ እርጋታ አሳጣ።

ዋለገ ግ ወሰለተ፤ ከስራው ላይ ሸለከ፣ ተሰርቆ ሄደ ።

ዋልጌ ቅ በስራው ላይ የማይገኝ፣ ወስላታ፤ አልምጥ ።

አዋለገ ግ 1. አወሰለተ፤ በስራው ላይ እንዳይገኝ አደረገ፣ ስራ አስፈታ። 2. አባለገ፣ አወሳሰተ።

ዋሊያ^{1} ስ አቶ፤ እግሮቹና አይኖቹ አካባቢ ፈካ ያለ፣ ከወደ ሆዱ ነጣ ብሎ ሌላው አካሉ ጥቁር ቡናማ የሆነ መልክና የተቀለበሱ ረጃጅም ቀንዶች ያሉት፣ ተራራማና ገደላማ በሆኑ ስፍራዎች የሚኖር፣ በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኝ ሳረበል የዱር እንስሳ(ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።

ዋሊያ^{2} ስ የማሽላ ሰብል እየበላች የምታስቸግር፣ ከርግብ አነስ የምትል ወፍ ።

ዋልሴ ስ ስለቱ እንደማጭድ በስተውስጥ የሆነ ጎባጣ ካራ ።

ዋልታ ስ 1. በመካከሉ የምሰሶ ጫፍ መግቢያ ሰፊ ቀዳዳና በዙርያው ብዙ ብስ ያለው፣ በስተላይ በኩል ውቅር ወይም ጭምጭማት የሚደረግበት የባጥ ገበታ፤ ጣራ መወጠኛ። 2. ጋሻ፤ መከታ። 3. መሬት የምትሽከረከርበት የሃሳብ ዘንግ ሰሜናዊ ወይም ደቡባዊ ጫፍ።

ዋልካ ስ መሬሬ፤ ጥቁር አፈር ።

ዋልጋ(ወልጌ) ስ የበግ ግልግል የሚበላ ቀበሮ መሰል አውሬ ።

ዋልጌ "**ዋለገ**" ስር ተመ.

ዋመሳ ስ ረዥም ጠር ።

ዋሜራ ስ በአንገትና በአንገት መካከል የሚገኝ የአገዳ አንዱ ክፍል፣ መለሊታው ።

ዋምራ ስ 1. ለውሃ መቅጃ፣ ለጠላ መያዣ የሚያገለግል ቅል። 2. ሸክና ።

ዋር ስ የጣቃ እጥፋት ።

ዋርሳ ስ ሚስት የባሏን ወንድም ወይም ወንዱ የወንድሙን ሚስት የሚጠራበት የተዛምዶ ስም ወይም በሁለቱ መሃል ያለ ባህላዊ ዝምድና ።

ዋርካ(ወርካ) ስ ከሾላ ፍሬ አነስ የሚልና ከበሰለ በኋላ ብዙውን ጊዜ ደረቅ ሲል የሚበላ ፍሬ ያለው፤ ቅጠሉ ሰፋፊ የሆነና እንጨቱ ነጣ ያለ ፈሳሽ የሚወጣው፣ ቅቅጥቅ ብለው በግንዱ ዙሪያ አግድም የሚንሰራፉ በርካታ ቅርንጫፎች ያሉት በጣም ትልቅ የሆነ ዛፍ።

ዋርዳ ስ 1. ጠቆር ያለ መልክ ያለው የወፍ አይነት። ቅ 2. ጠቆር ያለ መልክ ያለው (ለበቅሎ ወይም ለአህያ)።

ዋርዳ ሳሙና ስ ከጥቁርነት ፈገግ ያለ ወደ ቅላት የሚወስደው የበቅሎ መልክ ።

ዋርዴ የ"**ዋርዳ**"ን 2ኛ ፍች ተመ.

*ዋሰ^{1}

ዋስ ስ በእዳ፤ በወንጀል ወይም በሌላ ጉዳይ ተጠያቂ በመሆን የሚፈለግን ሰው ለማቅረብ፣ ካላቀረበም በእሱ ፈንታ ወይም ቦታ ለመጠየቅ

የውዴታ ግዴታ የሚገባ ሃላፊ፡ ተያዥ፡ መድን።

ዋስ ሰጠ ተያዥን ወይም ዋስ የሚሆነውን ሰው አቀረበ።

ዋስ በራሴ አለ እራሱን ለራሱ ዋስ አደረገ።

ዋስ ጠራ ዋስ ሰጠ፡ አቀረበ ።

ዋስ አጋች ስ የዋስን እቃ የሚይዝ፡ የሚወስድ፥ የሚያግት ሰው ።

ዋስ የለሽ ቅ ዋስ የማያገኝ፡ ወበላ (ሰው)።

ዋስትና ስ 1. ዋስ መሆን፡ ዋስነት። 2. የሚያስተማምን፡ አስተማማኝ የሚያደርግ ማረጋገጫ። *ስፖርትን ማዘውተር ለጤንነትና ለቅልጥፍና ዋስትና ነው።*

ዋስትናውን አወረደ ዋስነቱን ወይም ዋስ ለመሆን የገባውን ውል ሰረዘ ።

ዋስትና የሌለው ዘላቂነቱ፡ አገልግሎቱ የማያስተማምን ።

ተዋሰ ግ በእዳ፡ በወንጀል ወይም በሌላ ጉዳይ ተጠያቂ የሆነን ሰው ለማቅረብ፡ ካላቀረበም በእሱ ቦታ ለመጠየቅ የውዴታ ግዴታ ገባ፡ ሃላፊ፡ ተያዥ፥ መድን ሆነ ።

***ዋስ**²

ውሰት ስ ለባለቤቱ ተመላሽ የሚሆን እቃን፣...ለተወሰነ ጊዜ የመውሰድ ተግባር ።

ተዋሰ ግ በሗላ ለመመለስ ለጊዜው ብቻ በውሰት ወሰደ።

የተውሶ ቅ የትውስት፣ የራስ ያልሆነ፡ ለባለቤቱ ተመላሽ የሚሆን ።

አዋሰ ግ ለጊዜው ብቻ እንዲገለገልበት በውሰት ሰጠ ።

ዋስ "***ዋስ**¹" ስር ተመ.

ዋስትና ዝ.ከ.

ዋስዳ ስ 1. ብዙውን ጊዜ የከብት ስጋ ብልቶችን ከላዩ ላይ ለክቶ በማንጠልጠልና ለሁለት ተሸክሞ ከቦታ ወደ ቦታ ለማጓጓዝ የሚያገለግል እንደ አጠና ያለ እንጨት። 2. ከሃረግና ከመሳሰለው የሚሰራና ስጋን ማስቀመጫ የሚሆን ትልቅ ማቶት።

ዋሸ ግ 1. አበለ፡ ቀጠፈ፡ ሃሰት ተናገረ። 2. ተስፋ ሰጠ። *ልብስ እገዛልሻለሁ ብሎ ዋሽቶልኛል።*

ዋሾ ቅ ውሸታም፡ አባይ፡ ቀጣፊ፥ ሃሰተኛ።

ውሸት ስ ሃሰት፡ እብለት፡ ቅጥፈት።

ውሸቱ በቁመቱ ልክ ነው በጣም ዋሾ ነው።

ውሸቱ ቆሞ ይሄዳል በጣም ይዋሻል።

የውሸት የቀልድ ፡

የውሸት ጎራ ቅ ውሸታም ።

ውሸተኛ ቅ ሃሰተኛ፡ ቀጣፊ፡ አባይ ።

ውሸታም ዝ.ከ.

ዋሻ ስ 1. ተራራ፡ ገደል፡ ቋጥኝ፣...ባለበት አካባቢ በተፈጥሮ ወይም በሰዎች ወይም በአውሬዎች የተቆፈረ መኖሪያ፡ ጎሬ፡ ጉድጓድ። 2. መሸሸጊያ፡ መደበቂያ፡ መሰብሰቢያ። *የሌባ ዋሻ ነው።*

ዋሽንት ስ ውስጡ ክፍት ከሆነ ቀርከሃ ወይም ሸንበቆ፣...የሚሰራ አራትና ከዚያም በላይ ብሶች ያሉት ባህላዊ የትንፋሽ የሙዚቃ መሳሪያ።(ስእሉን የሙዚቃ መሳሪያ ስር ተመ.)።

ዋሽንት ይነፋል በዋሽንት ሙዚቃ ይጫወታል።

ዋሾ "**ዋሸ**" ስር ተመ.

***ዋበ**

ውብ ቅ ቆንጆ፡ ያማረ፥ የተዋበ፡ ሸጋ፡ ለዛ ያለው።

ውበት ስ 1. የመልክ፡ የድምፅ፡ የቅርፅ፡ የአቋቋም፣...ቁንጅና፡ ማማር፡ የመሳብ ሃይል፡ ለዛ። 2. የስነ ጥበብ ውጤት ማማር፡ ቁንጅና የመሳብ ሃይል።

ተዋበ ግ አማረ፡ ቆንጆ፡ ሸጋ ሆነ።

አስዋበ ግ አቆነጀ፡ አሳመረ፡ አስጌጠ።

ዋቢ ስ ሃላፊ፥ ተጠያቂ፡ ዋስ ።

ዋቢ መጻህፍት ስ በምርምር ፅሁፍ ጊዜ አገልግሎት ላይ የዋሉ፡ የተነበቡ የማመሳከሪያ መጻህፍት ።

ዋተተ ግ ተንከራተተ፡ ባተለ፡ ወዲያ ወዲህ አለ፡ ደከመ፡ ለፋ፡ ታከተ ።

አዋተተ ግ አንከራተተ፡ አባተለ፡ አደከመ፡ አለፋ ።

ዋነኛ "**ዋና**" ስር ተመ.

ዋና "**ዋኘ**" ስር ተመ.

ዋና ቅ 1. ሊቀ፡ ሃላፊ፡ ባለቤት፥ ቀዳሚ፡ ከሁሉም በላይ የሆነ፡ የበለጠ። 2. በጉልህ የሚታይ፡ የሚታወቅ፡ አስፈላጊ የሆነ። *ዋና ዋና ጉዳዮች ታይተዋል።* ስ 3. መነሻ፥ መነገጃ፡ መንቀሳቀሻ ገንዘብ (ትርፉን ሳይጨምር)።

ዋና ነው የዋዛ አይደለም ።

ዋናውን መለሰ ለንግድ የተገዛው እቃ፡ ድርጅት፣...የተገዛበትን ዋጋ መለሰ፡ አስገኘ ።

ዋና ሃሳብ ስ ፍሬ ነገር፡ ዋና መልእክት። *የፅሁፉ ዋና ሃሳብ ምንድን ነው?*

ዋና መስሪያ ቤት ስ ከሱ ሌሎች ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶች ያሉት የበላይ መስሪያ ቤት ።

ዋና መንገድ ስ ከሌሎቹ ይልቅ በርካታ ተመላላሾች የሚገለገሉበት ትልቅ መንገድ ።

ዋና ስራ አስኪያጅ ስ የአንድ ድርጅት የስራ አመራር ከፍተኛ ባለስልጣን፥ መሪ ።

ዋና በር ስ ከሌሎች አነስተኛና በየአቅጣጫው ከሚገኙ በሮች የተለየና ትልቅ የሆነ የፊት ለፊት በር ።

ዋና ከተማ ስ 1. ዋና ዋና መንግስታዊ መስሪያ ቤቶች፣ ድርጅቶች፣ ተቋሞች፣... የሚገኙበት የአስተዳደሩ ማእከል። 2. የአንድ አገር ርእሰ ብሄር የሚኖርበት የአገሪቱ ዋና መዲና።

ዋና ክፍል ስ ከመምሪያ በታች ሆኖ በስሩ የሚገኙትን የተለያዩ ክፍሎች ስራ የመምራት፣ የመቆጣጠር፣ የማስተባበር ስልጣን ያለው ክፍል።

ዋና ፀሃፊ ስ የአንድ ድርጅት የስራ አስፈፃሚ የበላይ ባለስልጣን።

ዋነኛ ቅ አይነተኛ፣ አስፈላጊ፣ ከሁሉም የበለጠ።

ዋናተኛ "**ዋኘ**" ስር ተመ.

ዋኔ ስ ርግብ የምትመስልና ከርግብ አነስ የምትል ወፍ(ስእሉን ወፍ ስር ተመ.)።

ዋንኬ [በግ] ስ ቆላ በሆነ አካባቢ የሚገኝ የበግ አይነት።

ዋንዛ ስ ፍሬው የሚበላ፣ እንጨቱ ጠንካራ፣ ቅጠሉ ሰፋፊ የሆነ ትልቅ ዛፍ።

ዋንጫ ስ 1. ከቀንድ፣ ከእንጨት፣ ከወርቅ፣ ከብር፣... የሚሰራ መጠጫ። 2. ከወርቅ፣ ከብር፣... የሚሰራና በስፖርት ወይም በሌላ ውድድር ላሸነፈ ወይም የበለጠ ውጤት ላገኘ የሚሰጥ ሽልማት።

ዋንጫ 1ኛ ፍቺ *ዋንጫ 2ኛ ፍቺ*

ዋንጫ ወሰደ አሸናፊ በመሆን ወይም በሌላ ምክንያት ዋንጫ ተቀበለ ።

ዋንጫ ልቅለቃ ስ በአንገት የሚወርዱት የእስክስታ አይነት ።

ዋንጫ አንጣጭ ስ ዋንጫ የሚሰራ ሰው ።

ዋኖስ ስ ርግብ የምትመስል ወፍ፥ ዋኔ ።

ዋኘ ግ በእጅ፣ በእግር፣ በክንፍ፣...እየቀዘፈ በባህር፣ በሃይቅ፣... ላይ ሄደ፥ ተንሳፈፈ።

መዋኛ ስ ለዋና አመች የሆነ ባህር፣ ሃይቅ፣... ወይም ለዋና ተብሎ የተዘጋጀ ሰፊ የውሃ ገንዳ ያለው ስፍራ።

ዋና ስ በእጅ፣ በእግር፣... እየተቀዘፈ በባህር፣ በወንዝ፥ በሃይቅ፣...ላይ የሚደረግ ጉዞ፣ እንቅስቃሴ፤ ውሃ ዋናም ይባላል።

የዋና ልብስ ስ በዋና ጊዜ የሚለበስ ልብስ።

ዋናተኛ ቅ ዋና አዋቂ።

አስዋኘ ግ መዋኘት አስቻለ። *ወንዙ ጥልቀት ስለሌለው አያስዋኝም።*

ዋካታ "***ወካ**" ስር ተመ.

ዋዋ ግ ጣመ፣ ጣፈጠ።

ዋዋቴ ስ ስሩ ሲያኝኩት በመጀመሪያ የሚመር፣ እየቆየ የሚጣፍጥ የእፀዋት አይነት።

አዋዋ ግ 1. ጥሩ ጣእም ሰጠ፣ አጣፈጠ። 2. ዋዋ።

ዋዛ ስ ቀልድ፣ ፌዝ፣ ዘበት፣ ቧልት፣ ጨዋታ። *ዋዛ አታብዛ ።*

እንደዋዛ ትኩረት ሳይሰጠው፣ እንደቀልድ፣ ሳይታሰብበት።

የዋዛ አይደለም በቀላሉ የሚታይ፣ የሚናቅ አይደለም።*እገሌ ምን ይመስላል እንጂ የዋዛ አይደለም* ።

ዋዛ ፈዛዛ ስ ቀልድ፣ ፌዝ። *በዋዛ ፈዛዛ ጊዜን ማባከን አይገባም* ።

ዋዘኛ ቅ ቀልደኛ፣ ፌዘኛ፣ ተጫዋች ።

ዋዘኛ መስሎ ሳይጠረጠር፣ ቁም ነገር ያለው ሳይመስል።

ተዋዛ ግ ተቃለደ፣ ተቃበጠ።

አዋዛ ግ 1. አታለለ፣ አማለለ፣ አዘናጋ፣ አጫወተ። 2. ቀስ ብሎ እያላመደ፣ በዘዴ ተጠቀመ (አንድን ነገር ለማድረግ)፤ አለሳለሰ፣ አባበለ። *መቀርቀሪያውን አዋዝተህ አስገባው።*

ዋዜማ ስ 1. ከዋና በአል ወይም ከአንድ ከሚጠቀስ ቀን አስቀድሞ የሚውል ቀን። 2. አንድ መንፈሳዊ ክብረ በአል ከሚከበርበት እለት አንድ ቀን ቀደም ብሎ በአሉን በሚመለከት በቤተክርስቲያን የሚዘመር ከሃያ ሁለቱ የድጓ አርእስተ ዜማዎች አንዱ ። 3. ባለ አምስት ቤት ቅኔ ።

ዋዠቀ ግ 1. ተንቃነቀ፣ ተወዛወዘ፣ ዋለለ። 2. አንድ አቋም አጣ፣ ወላወለ። 3. አንዴ ከፍ አንዴ ዝቅ አለ (ዋጋ፣...) ።

ዋገርቂ ቅ ወላዋይ ።

ዋኽርማ ስ ከብቶች ሲበሉት ሆዳቸውን የሚነፋ፣ ከሳር ጋር የሚበቅል አነስተኛ የእፀዋት አይነት ።

ዋኽንቢጥ(ዋኽንቢት) ስ ክንፎቿ ላይ ቀይ ያለባት፣ ጠቆር ያለች ነፍሳት ።

***ዋየ**

ውይይት ስ. 1. የሃሳብ ልውውጥ፥ ምክክር፥ ጭውውት። 2. ከሾፌሩ በስተሗላ አምስት አምስት ተሳፋሪዎችን የሚያስቀምጡ ሁለት የግራና የቀኝ አግዳሚ መቀመጫዎች ያሉት የከተማ ታክሲ መጠሪያ።

ተወያየ ግ 1. ሃሳብ ለሃሳብ ተለዋወጠ፥ አስተያየት ሰጠ፥ ተቀበለ። 2. ተነጋገረ፥ ተጨዋወተ፥ ተመካከረ።

አዋየ ግ 1. አስተዛዘነ፥ አጫወተ (በችግር፥ በመከራ ጊዜ)። 2. አማከረ ።

አወያየ ግ ሃሳብ ለሃሳብ አለዋወጠ፥ አነጋገረ ።

አወያይ ስ የስብሰባ፥ የውይይት መሪ፥ ሊቀመንበር።

ዋይ

ዋይታ ስ ጩሀት፥ እሪታ።

ዋይ አለ ግ ጮሀ፥ አለቀሰ ።

ዋይ የለሽ ግድ የለሽ፥ ሃሳብ የለሽ ለማለት የሚነገር።

ዋይክማ ስ የእንጨት ልጓም፥ ልጓጥ።

ዋዲያት(ዋድያት) ስ ብዙውን ጊዜ የሊጥ ማቡኪያ በመሆን የሚያገለግል ጎድጓዳ የሸክላ ወይም ተለቅ ያለ የእንጨት እቃ።

ዋጀ ግ 1. ገዛ። 2. ካሳ፥ ጉማ፥... ከፈለ (ከሞት፥ ከባርነት፥... ለማዳን)። 3 አዳነ ።

ዋጆ(ወጆ) ስ በሰው እጅ ለተገደለ ሰው የገዳይ ወገን ወይም ገዳዩ ለሟች ቤተሰብ የሚከፍለው የነፍስ ዋጋ፥ ካሳ፥ ጉማ (ገንዘብ፥ ከብት፥...) ።

ዋጅለት ስ ያልታረሰና አረም መጣያ ሆኖ የቆየ ለም መሬት ።

ዋገምት(ዋግምት) ስ የታመመ ሰው ገላ ከተበጣ በሗላ በበሽታ የተበከለ ደሙን መጦ ለማውጣት የሚያገለግል ከቀንድ የሚሰራ ባህላዊ የህክምና መሳሪያ።

ዋጊኖስ ስ በደጋ የሚበቅል መድሃኒትነት ያለው የሚባል የእፅዋት አይነት።

ዋጋ ስ 1. አንድ ነገር የሚገዛበት ወይም የሚሸጥበት፥ አንድ ስራ ለተሰራበት ወይም ለተሰጠ አገልግሎት የሚከፈል የገንዘብ መጠን፥ ልክ፥ ተመን። 2. ረብ፥ ጥቅም፥ ፋይዳ። *ዋጋ የለውም*። 3. ተገቢ፥ ተመጣጣኝ ቅጣት።
ዋጋውን አገኘ/ ዋጋዬን ሰጠኝ።

ዋጋ ሰቀለ ዋጋ አስወደደ።

ዋጋ ሰበረ መግዣ ዋጋውን አራከሰ፥ ዋጋ ቀነሰ።

ዋጋ ቆለለ ዋጋውን በጣም አበዛ፥ ከልክ አሳለፈ ።

ዋጋ ቆረጠ ዋጋውን ወሰነ፥ ርግጡን፥ መሸጫውን፥ መግዣውን ተናገረ።

ዋጋ አሳረረ መግዣ ዋጋውን ከፍ አድርጎ፥ ከሌላው አብልጦ ሰጠ (ተጫራቹ)።

ዋጋ አዋረደ መግዣ ዋጋውን አሳንሶ፥ ዝቅ አድርጎ ሰጠ (ገዥው)።

ዋጋ አፋረሰ በተነጋገረበት ዋጋ ሳይስማማ ቀረ፥ እንዳይሸጥ፥ እንዳይገዛ አደረገ።

ያለ ዋጋ በከንቱ፥ ያለጥቅም። *እዚህ ድረስ የደከምኩት ያለ ዋጋ ነው*።

ዋጋ ቢስ ቅ የማይረባ፥ ጥቅም የሌለው ።

ዋጋ የለሽ ዝ.ከ.

ዋጋ ያለው ከፍ ያለ ጠቀሜታ፥ ቁምነገር ያለው ።

የዋጋ ቅናሽ ከወትሮው፥ ከመደበኛው፥ ከነበረው ዋጋ ዝቅ ያለ የዋጋ መጠን ።

የዋጋ ንረት የ“**ዋጋ ግሽበት**”ን ተመ.

የዋጋ ውጣ ውረድ የዋጋ ከፍና ዝቅ ማለት፥ መዋዠቅ ።

የዋጋ ግሽበት የገንዘብ የመግዛት ሃይል መቀነስ፥ አጠቃላይ የሸቀጦች ዋጋ ማሻቀብ፥ የዋጋ ንረትም ይባላል።

ዋግ ስ ማሳ ላይ ያለ እህልን ወይብ የሚያስመስልና ፍሬ እንዳያፈራ የሚያደርግ የእህል በሽታ።

ዋግ መታው ዋግ እህሉን እንዳያፈራ አደረገው፥ አበላሸው።

ዋግምት "ዋገምት"ን ተመ.

ዋግንብ(ዋግምብ) ስ 1 ከእንጨትና ከሸንበቆ፥... የሚሰራ የድር አራዊ መወጠሪያና ማድሪያ። 2. የወጥመድ አይነት።

ዋጠ ግ 1.ወደ ሆድ አስገባ ፥ ሰለቀጠ። 2. አጠለቀ፥ አሰረገ፥ አሰመጠ (ጭቃ፥ ውሃ፥...ሰውን ወይም ሌላ ነገርን)። 3. በብዛት በላ። 4. አፍኖ ያዘ፥ ቻለ፥ ታገሰ። *ንዴቱን ዋጠ*። 5. ቻለ፥ አጠቃሎ ያዘ። *አዳራሹ ያን ሁሉ ሰው ዋጠው*። 6. ሸፈነ፥ ወረሰ። *ሰብሉን አረም ዋጠው*

ምን ዋጠው 1. ምን በጀው። 2. የት ሄደ፥ የት ጠፋ።

አልዋጥ አለው ነገሩን መቀበል፥ ማመን አቃተው።

ተዋጠ ግ 1. ጠለቀ፥ ሰረገ፥ ሰጠመ (በጭቃ፥ በውሃ፥...)። 2. ተወረረ፥ ተሸፈነ፥ ተጥለቀለቀ (ለምሳሌ ሰብል በአረም)። 3. ተጎረደ፥ ድምፁ ሳይሰማ፥ ሳይነበብ ቀረ (ፊደል፥ ቃለም፥...)። 4. ከብዙ ነገር ጋር በመደባለቁ ወይም አብሮ በመሆኑ መኖሩ የማይታወቅ ሆነ፥ ተሸፈነ።

አዋጠ ግ አበላ፥ አጎረሰ ።

ዋጣ ስ (የግ. አጠ.) አዝማሪ፥ ማሲንቆ ተጫዋች።

ዋሮጮ ስ በቆላ አካባቢ የሚበቅል ነጭ ግራር።

ዌ የ"ወ" ፈደል ሃምስ ዘር።

ው የ"ወ" ፈደል ሳድስ ዘር።

-ው¹ የተወሰነ ነገር አመልካች ምእላድ፤ መስተአምር። *ሰውዬው/ዝሆየው።*

-ው² 1. በግስ መጨረሻ እየገባ "እሱን" የሚለውን ተሳቢ የሚያመለክት ምእላድ። *ጠራው/ገደለው።* 2. በግስ መጨረሻ እየገባ "ለእሱ" የሚለውን ትርጉም የሚያመጣ ምእላድ። *ሰጠው/ነገረው።*

ውሃ ስ በዝናብ መልክ የሚወርድ፤ በምንጭነት የሚፈልቅና በሃይቅ፤ በኩሬ፤ በባህር፤ በወንዝ የሚገኝ ለመጠጥና ለሌሎችም አገልግሎቶች የሚውል ፈሳሽ፤ የሁለት እጅ ሃይድሮጅንና የአንድ እጅ ኦክስጅን ውሁድ።

በውሃ ይለቅ አዲስ ልብስ ለለበሰ ወይም ለገዛ ሰው የሚነገር ምርቃት።

ውሃ ሆነ 1. ቀጠነ፤ ጣእሙ፤ ሃይሉ ቀነሰ። 2. ደነገጠ፤ ክው አለ ። 3. ጠረሰ፥ አላንክ አለ (ጥርስ)። 4. ቀለጠ፤ ሟሟ።

ውሃ ቀጠነ አለ ምክንያት ሊሆን የማይችለን ነገር እንደምክንያት አድርጎ ጠብ ፈለገ ።

ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ የተለየ ውጤት የማይኖረው፤ ድርጊቱ ቢደጋገምም ውጤቱ ያው አንድ አይነት ነገር ብቻ በመሆኑ ልፋት እንጂ ለውጥ የሌለው።

ውሃ ቋጠረ 1. በተለያዩ ምክንያት (በህመም፤ በቃጠሎ፥...) ውሃ መሰል ፈሳሽ ያዘ፤ አዘለ (እጅ፤ እግር፥...)። 2. ውሃ ያዘ፤ አቆረ፤ አጠራቀመ (መሬቱ፤ መንገዱ፤...)።

ውሃ በላው 1. በውሃ ሙላት አደጋ ሞተ። 2. ድራሹ ጠፋ፤ የት እንደሄደ ሳይታወቅ ቀረ፤ እልም አለ። 3. መና፤ ከንቱ ሆኖ ቀረ።

ውሃ ቢወቅጡት እምቦጭ ለውጥ ለማስገኘት ጥረት ቢደረግም ተመልሶ ያንኑ ሆኖ መገኘት፤ አለመሻሻል፤ ለውጥ አለማሳየት ።

ውሃ አላየውም ፈፅሞ አልታጠበም፤ ውሃ አልነካውም።

ውሃ ወረደ ከወንዝ፤ ከምንጭ፤...ውሃ ለመቅዳት ሄደ።

ውሃ ወሰደው 1. በውሃ ሙላት አደጋ ሞተ። 2. በመጠጥ ሰከረ።

ውሃ ውሃ አለ 1. ቀጠነ፤ ሳይጣፍጥ ቀረ፥ ጣእም አጣ (ለምሳሌ ጠላ፤ ጠጅ፥...)። 2. ደከመ፤ አለከለከ (በመሮጥ፤ ዳገት በመውጣት፤...)።

ውሃ ውሃ አሰኘ አደከመ።

ውሃ ያነሳል ብዙ ውሃ ይፈልጋል (ለምሳሌ የሚቦካ ዱቄት)።

ውሃ ጠጣ ጠፋ፤ ቀለጠ፥ ታጣ (ገንዘቡ፤ ንብረቱ፤...)።

የውሃ መንገድ አደረገው ብዙ ጊዜ ተመላለሰበት።

የውሃ ሽታ ሆነ ጠፋ፤ ብዙ ጊዜ ሳይታይ ቆየ።

ውሃ ልክ ስ 1. የቤት ግድግዳ፤ ወለል፤...ትክክለኛና ቀጥ ያለ ገፅታ ይዞ መገኘትና አለመገኘት፤ አቀማመጡ በውሃ ወለል ልክ መሆንና አለመሆን። *ውሃ ልኩ አልተስተካከለም።* 2. ግድግዳ፤ ወለል፤...እባጣ ጎባጣ መሆን አለመሆኑ የሚለካበት፥ የሚዋልል ውሃ ውስጡ ያለበት ባለመስተዋት መሳሪያ። 3 በቤት ግድግዳ ስር ከውጪ በኩል ግድግዳውን አቅፎና ከመሬት ከፍ ብሎ ዙሪያውን የሚገነባ መደብ መሰል ግንብ።

ውሃ ሙላት ስ በዝናብ ምክንያት የሚመጣ ጎርፍ፥ ሃይለኛ ውሃ።

ውሃ ሰማያዊ ቅ ፈካ የሚል ሰማያዊ።

ውሃ ሽንት ስ ሽንት ብቻ (አይነ ምድርን የማይጨምር መሆኑን ለማመልከት)።

ውሃ ቀለም ስ በውሃ የሚበጠበጥ ቀለም ።

ውሃ አጣጭ ስ ባል ወይም ሚስት፤ የትዳር ጓደኛ ።

ውሃ ዋና "**ዋኘ**" ስር "**ዋና**"ን ተመ.

ውሃ ገብ ውሃ ያለበትና ለመስኖ እርሻ የሚያመች መሬት ።

ውሃ ጥርስ ስ የዐዳ ወይም እድፍ፥ ልማም የማይገኝ ጥርስ ።

[የ] ውሃ ቆጣሪ ስ ከቧንቧ የተጠቀሙበትን የውሃ መጠን የሚቆጥር፤ የሚመዘግብ መሳሪያ ።

የውሃ እናት ስ 1. በረጋ ውሃ ላይ የምትዋኝ፥ የምትበር ጠቆር ያለችና ከጥንዚዛ አነስ የምትል የነፍሳት አይነት። 2. (ዘይ.) ብዙ ውሃ የሚጠጣ ሰው ።

የውሃ ወፍጮ ስ በውሃ ሃይል የሚሰራ ወፍጮ።

የውሃ ጉድጓድ ስ ውሃ የሚቀዳበት ወይም የሚወጣበት ጉድጓድ ።

የውሃ ጋን ስ ለአንድ ለተወሰነ አካባቢ መገልገያ የሚሆን ውሃ ማጠራቀሚያ፥ ማከማቻ።

የውሃ ግድብ ስ ለተለያዩ አገልግሎት ሊውል የሚችል ወራጅ ውሃን አግዶ ለመያዝና በከፍተኛ መጠን ለማከማቸት የሚችል በግንብ የሚሰራ የውሃ መከተሪያ ።

የውሃ ጎማ ስ አትክልትን ውሃ ለማጠጣት፥ ውሃን ከአንድ ቦታ ስቦ ወደ ሌላ ቦታ ለመውሰድ፤...የሚያገለግል እንደ ቱቦ ሆኖ

በረጅሙ የተሰራና የሚጠቀለል ጎማ ።

የውሃ ጥም ስ የውሃ፡ የመጠጥ ፍላጎት ።

ውህደት "ዋሃደ" ስር ተመ.

ውለታ "ዋለ^2" ስር ተመ.

ውለን^1 ስ የጆሮ ያለመስማት ችግር፡ የጆሮ መዘጋት፡ መደንቆር ።

ውለናም ቅ (ስድብ) 1. ጆሮው የማይሰማ። 2. ደንቆሮ፥ ደደብ ።

ውለን^2 ስ ያልጥሩ የእህል ሰፍር፤ ድርብብ።

ውለኛ "ዋለ^2" ስር ተመ.

ውሊጥ ውሊጥ አለ ግ አንድ ጊዜ ወደ ግራ አንድ ጊዜ ወደ ቀኝ እያለ አስቸገረ፤ አንድ መስመር አልይዝ አለ።

ውላጅ "ወለደ" ስር ተመ.

ውል "ዋለ^2" ስር ተመ.

ውል

ውልታ ስ አምሮት፡ ትዝታ።

ውል አለ ግ እንደ ሑስ ትዝ አለ፥ አማረ፥ ተናፈቀ።

ውል ውል አለ ዝ.ክ.

ውልምጥምጥ "*ወለመጠ" ስር ተመ.

ውልቃት "ወለቀ" ስር ተመ.

ውልቅልቅ ዝ.ክ.

ውልብልቢት "*ወለበ" ስር ተመ.

ውልብልብ ዝ.ክ.

ውልብኝ ስ በእሳት ተጠብሶ የሚበላ የማሽላ እሸት ።

ውልክስ "ወልካሳ" ን ተመ.

ውልክፋ ስ መለል መለል ያለ ቁመና ያለው፥ ልጡ ለማሰሪያነት የሚያገለግል የጫፈታ ዛፍ አይነት ።

ውልክፍክፍ "ወለከፈ" ስር ተመ.

ውልውል "ወለወለ" ስር ተመ.

ውልግምት "ወለገመ" ስር ተመ.

ውልግድ "ወለገደ" ስር ተመ.

ውልግድግድ ዝ.ክ.

ውልፍስፍስ "ወለፈሰ" ስር ተመ.

ውሉ "ዋለ^1" ስር ተመ.

ውሉ አበል ዝ.ክ.

ውሪ ስ (የን.አነ.) ትንሽ ልጅ ።

ውሪያ ስ መልኩ ቢጫነት ያለው የወፍ አይነት።

ውራ ስ ስሩን ውስጥ ለውስጥ እየሰደደ የሚንሰራፋ የሳር አይነት።

ውራ ቅ በውድድር፥ በእሽቅድድም መጨረሻ የወጣ ፡

ውራጅ "ወረደ" ስር ተመ.

ውር^1

ውር አለ ግ ጠራ (ድመትን)።

ውሮ ለድመት መጥሪያነት የሚያገለግል ቃል፡

ውር^2

ውር ውር አለ ግ በብዛት ሳይሆን አልፎ አልፎ ሲንቀሳቀስ፥ ሲመላለስ ታየ።

ውርርድ "ወረደ" ስር ተመ.

ውርስ "ወረሰ" ስር ተመ.

ውርባ "ወረበ^2" ስር ተመ.

ውርንጭላ ስ የአህያ ግልገል፤ ውርንጫ እየተባለም ይጠራል ።

ውርደት "ወረደ" ስር ተመ.

ውርዴ ዝ.ክ.

ውርድ ዝ.ክ.

ውርጃ ዝ.ክ.

ውርጅብኝ ዝ.ክ.

ውርጋጥ ስ (የን.አኔ) ለአቅመ አዳም ያልደረሰ፡ ገና እድገቱን ያልጨረሰ፤ በአመለካከት፥ በአስተሳሰብ፥... ያልጎለመሰ ልጅ ።

ውርግርግ "*ወረገረገ" ስር ተመ.

ውርጭ "'ወረጨ^1" ስር ተመ.

ውሮ "ውር^1" ስር ተመ.

ውሰት "*ዋሰ^2" ስር ተመ.

ውሱን "ወሰነ" ስር ተመ.

ውሳኔ ዝ.ክ.

ውስ ጥጃን ለማባረር፥ የሚያገለግል ቃል።

ውስ አለ ግ ጥጃን ከለከለ፥ አባረረ፥ አገደ፤ ተው፡ ወይድ አለ።

ውስልትና "ወሰለተ" ስር ተመ.

ውስብስብ "*ወሰበሰበ" ስር ተመ.

ውስን "ወሰነ" ስር ተመ.

ውስኪ ስ እንደ ኣጃና ገብስ ከመሳሰለው የእህል ብቅል የሚሰራ፥ ከፍተኛ አልኮልነት ያለው መጠጥ።

ውስያን ስ የእቃ፥ የስጋ መስቀያ፤ ማንጠልጠያ።

ውስጥ መጥ. 1. የውጭ ተቃራኒ፥ በስተውጭ ያልሆነ። 2. ከሞላ ጎደል ዙሪያው ዝግ ሆኖ መሃሉ ክፍትነት፥ ባዶነት ያለው። *ጉድጓድ ውስጥ /ገደል ውስጥ/ ብርጭቆ ውስጥ።* 3. ለውጭ ወይም ለሌላ ሰው በግልፅ የማይታይ ነገር፥

ሁኔታ። *ውስጡን የማውቀው እኔ ነኝ፡* 4. በግልፅ፥ በይፋ ሳይሆን በምስጢር። *ትእዛዙን በውስጥ ሸረውታል።*

በ__ ውስጥ 1. በ___ ጊዜ። *በወር ውስጥ ሰርቶ ጨረሰው።* 2. በተወሰነ ቦታ፥ ክልል፥ አካባቢ። *በኢትዮጵያ ውስጥ የማይገኝ እቃ ገዝቶልኝ መጣ።* 3 መሃከል። *በእኔና በእሱ ውስጥ አትግባ፡*

ውስጡን ለቄስ 1. ገልጦ ሲያዩት፥ ጉዳዩን ሲረዱት የማይረባ። 2. ጉዳዩ ምስጢር ነው፥ ለሁሉ አይነገርም ለማለት የሚነገር።

ውስጠ ምስጢር ስ ድብቅ የሆነ፥ ያልታወቀ ምስጢር።

ውስጠ ወይራ ስ በቀላሉ ሊረዱት የማይቻል ምስጢር አዘል አነጋገር ።

ውስጥ ለውስጥ ሳይታይ፥ ሳይታወቅ በምስጢር ።

ውስጥ ልብስ ስ ሴቶች ከቀሚስ ስር የሚለብሱት ብዙውን ጊዜ ስስ የሆነ ገላ ነክ ልብስ ።

ውስጥ ሱሪ ስ ሙታንቲ፥ ገላ ነክ የሆነ አነስተኛ ሱሪ ።

ውስጥ አዋቂ ቅ 1. ቤተኛ፥ መውጫ መግቢያውንና ሁኔታውን የሚያውቅ፥ ሊጎዳ የሚችል (አብዛኛውን ጊዜ ለሌባ የሚነገር)። 2. ምስጢሩን በቅርብ የሚያውቅ።

ውስጥ እጅ ስ የእጅ ውስጠኛ ክፍል፥ መሃል እጅ (ስእሉን እጅ ስር ተመ.)።

ውስጥ እግር ስ መሬት የሚረግጠው ውስጠኛው የእግር ክፍል።

ውስጥ ውስጡን ይፋ ሳይሆን፥ በድብቅ።

የውስጥ በሽታ በውጫዊ አካል ላይ የማይታይ በሽታ (ለምሳሌ የልብ፥ የአንጀት በሽታ)።

የውስጥ ጉዳይ ሌሎች እንዲገቡበት የማያስፈልግ የራስ ጉዳይ፤ በባለቤቱ ብቻ ሊፈታ የሚገባው የግል ችግር (ብዙውን ጊዜ ለሃገር) ።

ውስጠኛ ቅ ከውስጥ ያለ፥ በውስጥ በኩል የሆነ።

ውስጣዊ ቅ 1. የግል፥ የራስ የሆነ። *ውስጣዊ ችግራችንን እራሳችን እንፈታዋለን፡* 2. በግል፥ እርስ በእርስ፥ በምስጢር። *ውስጣዊ ስምምነት አድርገዋል።* 3. የውስጥ።

ውሸተኛ "ዋሸ" ስር ተመ.

ውሸታም ዝ.ከ.

ውሸት ዝ.ከ.

ውሻ ስ 1. ከሰው ጋር አብሮ የሚኖር፥ የጌታውን ቤትና ንብረት የሚጠብቅ ለማዳ አውሬ፤ ሰው ወዳጅ፤ ቤት ጠባቂ፥ ያልለመደው ሰው ወይም አውሬ ሲመጣ የሚጮህ፤ የሚናከስ። 2. (ስድብ) ልክስክስ፤ ተለማማጭ (ስእሉን የቤት እንስሳ ስር ተመ.)።

የውሻ ቁስል ያድርግልህ ቁስሉ ቶሎ ይዳንልህ ለማለት የሚነገር ምርቃት ።

ውሻ በጨው የማይቀምሰው (ዘይ.) አስቀያሚ፥ የማይረባ፤ የማይፈለግ ።

ውሻ ሆድ (ዘይ.) የማይጨክን፥ የማይቆርጥ፤ ቂም የማይዝ።

የውሻ ምላስ ስ 1. መልኩ ጥቁር አረንጓዴ ሆኖ መለል መለል ብሎ የሚበቅልና በግራ በቀኝ እሾህ ያለው ጠፍጣፋ የእፅዋት አይነት። 2. ጠፍጣፋ ሆኖ በጣም የሳሳ (ብዙውን ጊዜ ለእንጀራ)።

የውሻ ስንደዶ ስ ስንደዶ የሚመስል የሳር አይነት።

የውሻ በሽታ ስ በንክሻ የሚተላለፍ፥ የሚያሳብድና ካልታከሙት እስከሞት ሊያደርስ የሚችል የደመ ሞቃት እንሰሳት የነርቭ ስርአት በሽታ ።

የውሻ ዝምብ ስ ተርብ ።

ውሻል ስ 1. በጎደለ መሙሊያ ወይም የነገር ጭማሪ። 2. ሽብልቅ። 3. (ስድብ) እራሱን ያልቻለ፥ ለማሟያነት የሚገባ። 4. የሳሳ እስርን ለማጥበቅ የሚገባ አነስተኛ ውታፍ።

ውሽልሽል "ወሸለ" ስር ተመ.

ውሽማ "ወሸመ" ስር ተመ.

ውሽሽ ስ ሰሩ ድንች የሚመስል የተክል አይነት።

ውሽባ "ወሸባ^{2}" ን ተመ.

ውሽንፍር ስ ንፋስ የተቀላቀለበት አገድም የሚዘንብ ዝናብ፤ ወጨፎ።

ውቂያ "ወቃ" ስር ተመ.

ውቃሪ "ወቀረ" ስር ተመ.

ውቃቢ ስ 1. ከእያንዳንዱ ሰው ጋር አብሮ ይኖራል የሚባል ጠባቂ መልአክ፤ ውቃቢ አምላክም ይባላል። 2. ዛር፥ ርኩስ መንፈስ።

ውቃቢ ራቀው 1. ቀላቢስ ሆነ፥ ተጎሳቆለ። 2. በረከት አጣ ።

ውቃቢ ቀረበው 1. ጥሩ ነገር ገጠመው፥ ተሳካለት። 2. የተረጋጋ ጨዋ ሰው ሆነ፤ ግርማ ሞገስ አገኘ ።

ውቃቢ አስራቀው 1. አስደነገጠው (በውበት፥ በስድብ፥...)። 2. በረከት አሳጣው።

ውቃቢው ተገፈፈ በጣም ደነገጠ።

ውቃቢው አልወደደውም ደስ አላለውም፥ አስጠልቶታል (ያየው፥ የተመለከተውና

የቀረበለት፥… ነገር)።

ባለውቃቢ ስ ውቃቢ ያለበት፡ ጠንቋይ፡ ባለዛር።

ውቃቢ ቢስ ጥላቢስ፥ ነጠላ፡ ቀትረ ቀላል፡ ግርማ ሞገስ የሌለው ።

ውቃቢ የለሽ ዝ.ከ.

ውቃጭ "ወቀጠ" ስር ተመ.

ውቅራት "ወቀረ" ስር ተመ.

ውቅር ዝ.ከ.

ውቅያኖስ ስ 1. የመሬትን ሶስት አራተኛ የሚሸፍን፡ ጥልቅና በጣም ሰፊ የሆነ ባህር (እንደ አትላንቲክና ህንድ ውቅያኖስ የመሳሰለው)። 2. (ዘይ.) ጥልቅ፡ ሰፊ።

ውቅጥ "ወቀጠ" ስር ተመ.

ውበት "*ዋበ" ስር ተመ.

ውብ ዝ.ከ.

ውታፍ "ወተፈ" ስር ተመ.

ውትርትር "*ወተረ" ስር ተመ.

ውትብትብ "*ውተበተበ" ስር ተመ.

ውትወታ "ወተወተ" ስር ተመ.

ውትፍትፍ "ወተፈ" ስር ተመ.

ውን

ውን ውን አለ ግ 1. ተንቀነቀ፡ ተወዛወዘ (ጭራ)። 2. ወዲያ ወዲህ አለ፡ ተዘዋወረ (የደከመ ሰው)።

ውንብድና "ወነበደ" ስር ተመ.

ውንክርክር "*ወነከረ" ስር ተመ.

ውካታ "*ወካ" ስር ተመ.

ውክልና "ወከለ" ስር ተመ.

ውዝት "ወዘተ" ስር ተመ.

ውዝዋዜ "ወዘወዘ" ስር ተመ.

ውዝግብ "*ወዘገበ" ስር ተመ.

ውዝፍ "ወዘፈ" ስር ተመ.

ውኾርሞ ስ ውስጠ ክፍትና ረዥም የሆነ፥ በጋያ የሚጨስ ትንባሆ መጠጫ (ሸንበቆ፡ ቧንቧ፡…)።

ውይይት "*ዋየ" ስር ተመ.

ውዳሴ "ወደሰ" ስር ተመ.

ውዳቂ "ወደቀ" ስር ተመ.

ውዴላ "ወደለ^{2}" ስር ተመ.

ውዴታ "ወደደ" ስር ተመ.

ውድ ዝ.ከ.

ውድማ ስ ሜዳ፡ ደን የወረሰው፡ ሰው የማይኖርበት መሬት።

ውድማ "አውድማ" ን ተመ.

ውድቀት "ወደቀ" ስር ተመ.

ውድቅ ዝ.ከ.

ውድቅት ዝ.ከ.

ውድን "ወደነ" ስር ተመ.

ውድንቢ ስ መልኩ ወርቅማ ሆኖ በጀርባው ላይ ነጫጭ ሸንትሮች ያሉበት፡ ጠመዝማዛ ቀንድ ያለው፥ ሜዳ ባለበት ቆላማ ስፍራዎች መንጋ ሆኖ የሚታይና ስጋው ለምግብነት የሚያገለግል የዱር እንስሳ (ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።

ውድድር "*ወደረ" ስር ተመ.

ውጉዝ "*ወገዘ" ስር ተመ.

ውጊያ "ወጋ" ስር ተመ.

ውጋት ዝ.ከ.

ውጋገን "ወገግ" ስር ተመ.

ውጋጋን "ወገን" ስር **"ውጋገን"** ን ተመ.

ውግ "ወጋ" ስር ተመ.

ውግዘት "*ወገዘ" ስር ተመ.

ውጤት "ወጣ" ስር ተመ.

ውጥረት "ወጠረ" ስር ተመ.

ውጥኔ ስ ወደ ብርቱካንነት መልክ የሚቀርብ ደቀይና የቢጫ ቅልቅል የሆነ የቀለም አይነት ።

ውጥን "ወጠነ" ስር ተመ.

ውጥንቅጥ ቅ የተቀላቀለ፡ የተቀያየጠ፡ የተደባለቀ።

ውጥንቅጡ ወጣ ተመሰቃቀለ፡ ተደበላለቀ።

ውጪ "ወጣ" ስር **"ውጭ"** ን ተመ.

ውጭ "ወጣ" ስር ተመ.

ውፉሬ "ወፈረ" ስር **"ውፍረት"** ን ተመ.

ውፍረት "ወፈረ" ስር ተመ.

ዎ የ"ወ" ፊደል ሳብእ ዘር ።

-ዎ (-ዎት) (የአክብሮት አጠቃቀም) የሁለተኛ መደብ፥ ነጠላ ቁጥር አገናዛቢ ምእላድ። *መፅሃፍዎ።*

-ዎች "-ኦች" ን ተመ.

ዘ

ዘ ከ"ወ" ፊደል ቀጥሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል (ግእዙ ዘሂ) ።

ዘሃ "ዝሃ" ን ተመ.

ዘለለ ግ 1. ወደ ላይ እንጣጥ አለ። *ዘሎ የቤቱን ጣራ በእጁ ነካ*፡ 2. እመር አለ፡ እግሮቹን ከመሬት ከፍ አድርጎ በማንሳት ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ተንቀሳቀሰ፡ ተሻገረ። *የቦዩን ውሃ በእግሩ ሳይነካ ዘሎ ተሻገረ*። 3. ተጫወተ፥ ቦረቀ፡ ጨፈረ። 4. አለፈ፡ ተወ። *ሶስተኛውን ገፅ ዘሎ አራተኛውን አነበበ*፡ 5. ከተወሰነው መጠን አለፈ፡ ከፍ አለ፥ በለጠ።

ዘለህ አትሳደብ ያለምክንያት፡ ከመሬት ተነስተህ አትሳደብ።

ዝላይ ስ 1. ጭፈራ፡ ጨዋታ። 2. መዝለል፥ እንጣጥ ማለት።

ዘለል አለ ግ ሳቅ ብሎ ታየ፥ በለጥ አለ።

ተዘለለ ግ ታለፈ፡ ተረሳ፥ ተተወ ።

የማይዘለል የማይተው፡ የማይታለፍ፡ ቸል የማይባል።

ተዛለለ ግ ተጫወተ፥ ተሳፋ ።

መዛለያ ስ 1. መረማመጃ፡ መሸጋገሪያ። 2. የልጆች መጫወቻ ቦታ ።

ዘለለ^2 ግ በበሰለ ወይም በተብላላ ድፍድፍ ላይ ውሃ ጨመረ፡ ሞላ፡ ሸመ ።

ዝልል ስ በበሰለ ወይም በተብላላ ድፍድፍ ላይ ውሃ ከተሞላበት በኋላ ወዲያው በውንፊት ተጣርቶ ሊጠጣ የሚችል የጠላ አይነት ።

ተዘለለ ግ በበሰለ ወይም በተብላላ ድፍድፍ ላይ ውሃ ተጨመረ፡ ተሞላ፡ ተሸመ ።

ዘለላ ስ 1. (የእንባ) አነስተኛ ጠብታ። 2. ፍሬ የተሸከመች አነስተኛ ቅርንጫፍ። *የወይን ዘለላ* ።

ዘለሰ ግ 1. ቆረጠ፡ ጣለ፡ አጋደመ፡ ለሸለሸ (ዛፍን)። 2. አቀረቀረ፡ ደፋ (አንገትን)።

መዘለሻ ስ አነስተኛ መጥረቢያ ።

ዘለሰኛ ስ ግጥሙ ባለ ሁለት ቤት የሆነ፡ ቀበና ዝግ ወይም ረገብ ተደርጎ የሚዜም የመሰንቆ ምትና ዜማ ።

ዘለቀ ግ 1. መጣ። *ወደዚህ መቼ ትዘልቃለህ?* 2. አንድን ነገር ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ አከናወነ፡ ጨረሰ፡ ተወጣ። 3. ራቀ። *ዘልቆ ሄደ።* 4. ቆየ፡ ከረመ፡ ሰነበተ። *ክረምቱን አብሮን ዘለቀ።* 5 ከአንድ ወገን ጫፍ በመነሳት፥ በውስጥ በኩል አልፎ በሌላው ወገን ጫፍ በኩል ታየ፡ ብቅ አለ።

ዘልቆታል 1. ገብቶታል፡ በደንብ አውቋል። *ትምህርቱ ዘልቆታል*። 2. እስከ መጨረሻው ሄዷል።

ዘለቃ ስ 1. ዘለአለም፥ መጨረሻ። *እስከ ዘለቃው አንገናኝም*፡ 2. ወደፊት። *ያለፈው አልፏል! ለዘለቃው ግን አስብበት* ።

ዘለቄታ ስ ዘለቃ።

ዘለቄታ የለውም አይቆይም፡ እድሜ የለውም።

ለዘለቄታው ለወደፊቱ፡ እስከመጨረሻው።

ዘላቂ ቅ እስከ መጨረሻ የሚሄድ፡ የሚቆይ።

ዝለቅ ግ ግባ፡ ጎራ በል።

ተዘለቀ ግ ተከናወነ፥ ተፈፀመ፡ ተጨረሰ።

አይዘለቅም በቀላሉ አይገፋም፡ ያስቸግራል፥ እንዲህ በዋዛ የማይወጡት አይደለም።

ተዛለቀ ግ ተቻችሎ ኖረ፡ ቆየ።

አዘለቀ ግ አቆየ፡ አከረመ፡ አሰነበተ፥ የተወሰነ ጊዜ አደረሰ።

አዛለቀ ግ 1. እስከ መጨረሻው አብሮ ሆነ፡ ቆየ። 2. አዋጣ፡ ጠቀመ። *ሁሌ መጠጣት አያዛልቅም*።

ዘለበት ስ ከብረት፥ ከፕላስቲክ ወይም ከቀንድ፥... የሚሰራ የቀበቶ፥... መቆለፊያ።

ዘለባብዳ "**ዘላበደ**" ስር ተመ.

ዘለንጋ ስ ከግድግዳ ጋር ተያይዞ ከእንጨትና ከጭቃ የሚሰራ የእቃ መደርደሪያ።

ዘለአለም (**ዘላለም**) ተው.ግ. ሁልጊዜ፥ ዘውትር።

ዘለአለማዊ ቅ 1. ቋሚ፥ ኗሪ። 2. መጨረሻ፥ ፍፃሜ የሌለው።

ዘለዘለ ግ 1. ቁራጭ ስጋን በስለት እየሰነጠቀ በመሸንሸን ቅጥነትና ርዝማኔ እንዲኖረው አደረገ። 2. በጥርሱ ነከሰ፥ ዘነተረ (አካልን)።3. (ዘይ.) አማ፡ አባጨ (ሰውን)።

ዘለዘል(ዘልዘልቱ) ቅ (ስድብ) 1. ዘልዛላ። 2. ዘዋሪ፡ ስራ ፈት፥ ማጋጣ።

ዘልዛላ ቅ 1. (ስድብ) ባለጌ፡ ስድ አደግ። 2. (ስድብ) ዘዋሪ፥ ስራ ፈት። 3. ያለአግባብ በጣም የረዘመ (ለምሳሌ ልብስ)።

ዝልዝል ስ የተዘለዘለ ስጋ።

ተንዘለዘለ ግ ተንጠለጠለ፡ ውዝውዝ አለ።

ተንዘላዘለ ግ 1. ስራ ፈቶ ወዲያ ወዲህ አለ፥ ባለገ። 2. አለቅጥ ረዘመ።

አንዘለዘለ ግ አንጠለጠለ፡ ውዝ ውዝ እንዲል አደረገ።

አንዘላዘለ ግ በአስተዳደግ ጉድለት አባለገ ።

ዘለገ ግ ረዘመ፡ በለጠ፥ ከፍ አለ (በቁመት) ::

ዘለግላጋ ቅ መለሉ፡ ረጅም ቁመት ያለው ::

***ዘለገለገ**

ዝልግልግ ቅ ምልግልግ ::

ዝልግልግ አለ ግ ተዝለገለገ፥ ማለገ፡ ሙልጭልጭ አለ ::

ተዝለገለገ ግ እንደለሃጭ ተጎተተ፥ ተምለገለገ፥ ማለገ::

አዝለገለገ ግ አምለገለገ፡ አዝረበረበ::

ዘለግላጋ "**ዘለገ**" ስር ተመ.

ዘለጎሰ ግ ሲፅፍ ወይም ሲያነብ ቃልን፡ ፊደልን፥... እየዘለለ፡ እየገደፈ ፃፈ፡ አነበበ::

ዝልጉስ ቅ 1. ሀጥንቃቄ ያልተፃፈ፡ የተገደፈ (ፅሁፍ):: 2. ጥንቃቄ የሌለው፡ ግድ የለሽ::

ዘለፈ^{1} ግ ነቀፈ፡ ሰደበ::

ዘለፋ ስ ነቀፋ፡ ስድብ፥ ቁጣ::

ዝለፊያ ዝ.ከ.

ዘለፈ^{2} ግ 1. ዘለሰ፡ ጣለ፥ አጋደመ(ዛፍን፥...):: 2. ዘንበል፥ ደፋ አደረገ (አንገትን)::

መዘለፊያ ስ ትንሽ መቀረቢያ::

***ዘለፈለፈ**

ዝልፍልፍ(ዘለፍላፋ) ቅ 1. አቅመቢስ፥ ደካማ:: 2. ለስላሳ፥ ዝንፍልፍል::

ዝልፍልፍ አለ ግ ተዝለፈለፈ::

ዝልፍልፍ አደረገ ግ አዝለፈለፈ::

ተዝለፈለፈ ግ ዛለ፥ አቅም አጣ፡ ደከመ፡ ተልፈሰፈሰ::

አዝለፈለፈ ግ አዛለ፡ አቅም አሳጣ፥ አደከመ::

ዘለፋ "**ዘለፈ**" ስር ተመ.

ዘለፍላፋ "***ዘለፈለፈ**" ስር "**ዝልፍልፍ**"ን ተመ.

ዘላለም "**ዘለአለም**" ን ተመ.

ዘላቂ "**ዘለቀ**" ስር ተመ.

ዘላበደ ግ ያልተያያዘና እውነትነት የሌለው ነገር ተናገረ፥ ቀባጠረ፥ ቀላመደ::

ዘላባጅ ቅ ቀላማጅ፡ ቀባጣሪ::

ዘለባብዳ ዝ.ከ.

ዘላን ስ 1. አንድ ቦታ ላይ ቋሚ የሆነ መኖሪያ ቤት የሌለው፥ ለከብቶቹ ሳርና ውሃ ለማግኘት ሲል እንደየወቅቱ ሁኔታ ከቦታ ወደ ቦታ እየተዘዋወረ የሚኖር ህዝብ:: 2. (ዘይ.) ተቆጣጣሪና ቋሚ አድራሻ የሌለው፡ በፈለገበት የሚያድር ሰው::

ዘልቆስታል "**ዘለቀ**" ስር ተመ.

ዘልዘሉቱ "**ዘለዘለ**" ስር "**ዘልዛላ**" ን ተመ.

ዘልዛላ "**ዘለዘለ**" ስር ተመ.

ዘመመ^{1} ግ 1. አዘነበለ፥ አጋደለ:: 2. ዝማሜ ተብሎ የሚጠራውን የዜማ ስልት ተከትሎ መቋሚያውን (ዘንጉን) ወደግራና ወደቀኝ፡... በማወዛወዝ አብሮ እየተንቀሳቀሰ አዜመ(ደብተራ)::

ዝማሜ ስ ከሰውነትና ከመቋሚያ ውዘዋዜ ጋር እየተቀናጀ የሚዜም የአቋቋም የዜማ ስልት::

አዘመመ ግ አዘነበለ፥ አጋደለ::

አዝማሚያ ስ ዝንባሌ፥ አካሄድ፥ አቅጣጫ (የነገር፥ የእስትሳሰብ፥ የፍላጎት፥...)::

ዘመመ^{2} ግ የእህልን ነዶ ሞላላ ቅርፅ አስይዞ ከመረ::

ዘመሚት ስ ቀላ የሚልና ምስጥ ወይም ጉንዳን የሚመስል ነፍሳት::

ዘመረ ግ በድምፁ እያዜመ አመሰገነ፡ አወደሰ፡ ዜማን አሰማ::

መዘምር (ብ.ቁ. **መዘምራን**) ስ በዜማ የሚያወድስ፡ የሚያመሰግን፥ የዜማ ባለሙያ የሆነ ደብተራ::

መዝሙር ስ 1. በዜማ የተዘጋጀና እሁድ እሁድ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የሚዘመር የያሬድ ድርሰት:: 2. ከላይ የተጠቀሰውን ድርሰት የያዘ መፅሃፍ:: 3. የተወሰነ የዜማ ስልት ተከትሎ በድምፅ የሚዜም መንፈሳዊ ወይም ስጋዊ ድርሰት::

መዝሙረኛ ስ ዘማሪ፥ መንፈሳዊ ወይም አለማዊ የመዝሙር ድርሰትን በዜማ የሚያሰማ (ሰው)::

ዘማሪ (ብ.ቁ **ዘማርያን**) ስ መዝሙርን በዜማ የሚያሰማ፡ መዝሙረኛ::

ዝማሬ ስ 1. ዜማ:: *የወፎቹ ዝማሬ ከሩቅ ይሰማል*:: 2. በዜማ የሚቀርብ ውዳሴ፥ ምስጋና:: 3. ከእጣን ሞገር በፊት በቅኔማህሌት የሚባል ያሬዳዊ የዜማ ድርሰት::

ዝማሬ መዋስእት ስ ዝማሬና መዋስእት የሚባሉትን የያሬድ ድርሰቶች በአንድነት የያዘ የዜማ መፅሃፍ::

አዘመረ ግ1. ማሲንቆ እየመታ በዜማ ግጥም ደረደረ፥ ዘፈነ (አዝማሪ):: 2. መሀ፥ ፎከረ፡ ደነፋ::

አዝማሪ ስ 1. በባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች እየታጀበ በመዝፈን የሚተዳደር (ሰው):: ቅ 2. (ስድብ) ምላሰኛ፥ ተሳዳቢ::

ዘመተ ግ 1. ሄደ፥ ተጓዘ (ለጦርነት፡ ለውጊያ ወይም ለሌላ ተግባር):: 2. ተሰፋፋ፥ ቲናኘ፡ ተሰራጨ (በሽታ፡ ወሬ፥...):: 3. ተንሰራፋ፥

ተራባ (አትክልት፣...)።

ዘመቻ ስ 1. ለጦርነት የሚደረግ እንቅስቃሴ፣ ጉዞ። 2. በተወሰነ ጊዜ ውስጥ እንዲጠናቀቅ በህብረትና በርብርቦሽ የሚከናወን ተግባር።

ዘማች ስ ወደ ዘመቻ ለመሄድ በዝግጅት ላይ ያለ ወይም የዘመተ ሰው።

ዘማች አሞራ ስ ወቅቶችን እየጠበቀ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በመዘዋወር የሚኖር የአሞራ አይነት።

ተዘመተ ግ ተራባ፣ ተስፋፋ፣ ተናኘ (በሽታ፣ ወሬ፣...)።

አዘመተ ግ 1. በጦርነት ወይም በሌላ ስራ ላይ አሰማራ። 2. ግንዱ የራሱን ስርና ቅርንጫፍ በማውጣት እየተራባ እንዲሄድ ለማድረግ ከስሩ ሳይነቀል ቅርንጫፉን አፈር ውስጥ እንዲጋደምና ከወደ ላዩ ብቻ ቀጥ ብሎ እንዲቆም በማድረግ አራባ።

አዝማች ስ 1. የዘማቾች አለቃ ወይም መሪ። 2. በዜማ፣ በዘፈን ወይም በግጥም ስንኞች መካከል አልፎ አልፎ ጣልቃ እየገባ በመደጋገም የሚባል የዜማ፣ የዘፈን፣ የግጥም ቃል ወይም ሃረግ።

አዘመተ ግ 1. አሰራጨ፣ አዳረሰ፣ ነዛ። 2. አለማ፣ አራባ፣ አባዛ።

ዘመነ(ዘበነ) ግ ዘመናይ ሆነ።

ዘመን(ብ.ቁ.**ዘመናት**) ስ ጊዜ፣ ወቅት፣ አመት።

ለዘመናት ለረጅም ጊዜ፣ ለብዙ አመታት።

ዘመነ ሃዲስ ስ ከክርስቶስ ልደት ወዲህ ያለው ጊዜ፣ ዘመን።

ዘመነ ሉቃስ ስ በዘመነ ማርቆስና በዘመነ ዮሃንስ መካከል ያለው አመት፣ ጊዜ፣ ዘመን።

ዘመነ መሳፍንት ስ በኢትዮጵያ ከአስራ ስምንተኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ እስከ አስራ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ድረስ ስልጣን በመሳፍንት ተከፋፍሎ የነበረበት ጊዜ።

ዘመነ ማርቆስ ስ በዘመነ ማቴዎስና በዘመነ ሉቃስ መካከል ያለው አመት፣ ጊዜ፣ ዘመን።

ዘመነ ማቴዎስ ስ በዘመነ ዮሃንስና በዘመነ ማርቆስ መካከል ያለው አመት፣ ጊዜ፣ ዘመን ።

ዘመነ ብሉይ ስ የኦሪት ዘመን ።

ዘመነ አስተርእዮ ስ ከጥምቀት (ከጥር 11 ቀን ጀምሮ) እስከ ሁዳዴ ፆም መግቢያ ያለው ወቅት፣ ጊዜ።

ዘመነ እንኮዬ ስ በማንኛውም በኩል ችግር የሌለበት ደግ ጊዜ ።

ዘመነ ዮሃንስ ስ በዘመነ ሉቃስና በዘመነ ማቴዎስ መካከል ያለው ጊዜ፣ ዘመን፣ አመት ።

ዘመነ ግርንቢጥ/ግልምቢጥ ስ እውነት የጠፋበት፣ ሃሰት የሰፈነበት ጊዜ፤ ነገሩ ሁሉ የተገላቢጦሽ የሆነበት፣ የነበረው ባህል፣ ልምድ፣... የተለወጠበት ጊዜ።

ዘመነ ፅጌ ስ ከመስከረም 26 እስከ ህዳር 6 ቀን ያለው ጊዜ፤ የአበባ ወቅት።

ዘመን መለወጫ ስ የአመቱ የመጀመሪያ ቀን፤ እንቁጣጣሽ፤ እንደ ኢትዮጵያ የቀን አቆጣጠር መስከረም አንድ ቀን።

ዘመን አመጣሽ ቅ አዲስ የተፈለሰፈ፣ የተሰራ፣ የመጣ፣ የታየ፣ የተገኘ ።

ዘመናዊ ቅ 1. በአይነቱ ወይም በሁኔታው አዲስ የሆነ። 2. በወቅቱ ያለውን አዲስ ሁኔታ (የአስተሳሰብ፣ የአኗኗር፣...) የሚከተል ።

ዘመናይ (ዘበናይ) ቅ 1. ባለጊዜ፣ እንደፈለገው ለመሆን ጊዜ ያመቸው፣ ኑሮው የተሳካለት። 2. የ"**ዘመናዊ**"ን 2ኛ ፍቺ ተመ.

ዘመዘመ ግ 1. ለቁልፍ (ለአዝራር) ማስገቢያ ተብሎ በልብስ ላይ የሚበጅ የቀዳዳዎችን አፍ፣ የልብስን ጠርዝ ወይም ክፈፍ፣... በክር ቀመቀመ። 2. በበርኖስ፣ በጨርቅ፣...ላይ የጥልፍ ስራ ሰራ፣ ጠለፈ።

ዘምዛሚ ስ የዝምዝማት ስራ ባለሙያ።

ዝምዝማት(ዝምዝም) ስ በጨርቅ ወይም በበርኖስ፣...ላይ የሚሰፋ ቅምቅማት፤ ጥልፍ ።

ተዘመዘመ ግ 1. ዳር ዳሩ በክር ተሰፋ፣ ተቀመቀመ። 2. ጥልፍ ተጠለፈበት (በጨርቁ፣ በበርኖሱ፣... ላይ)።

*ዘመደ

ዘመድ ስ 1. በትውልድ የአባት ወይም የእናት ወገን የሆነ ሰው (ለምሳሌ አጎት፣ አክስት፣ የአጎት ወይም የአክስት ልጅ)። 2 ወዳጅ ።

ዘመድ አፈራ/አበጀ/ገዛ ዘመድ፣ ወዳጅ አገኘ።

ዘመድ አዝማድ ስ ተወላጅ፣ ዝርያ፣ ወገን፤ ቁጥሩ በርከት ያለ ዘመድ።

የዘመድ ዋጋ ስ በዝምድና፣ በወዳጅነት ወይም በመተዋወቅ የተነሳ አንድን ነገር ከተወሰነው ዋጋ በመቀነስ ለገዥው የሚሸጥበት ዋጋ።

ዝምድና ስ 1. ተዛምዶ፣ የዘር ወይም የትውልድ ግንኙነት። 2. መመሳሰል፣ ግንኙነት። *ዝምድና ያላቸው ሃሳቦች የበለጠ ቢብራሩ መልካም ነው።*

ተዛመደ ግ 1. ተወዳጀ፣ ተስማማ። 2. ተቀላቀለ፣ ተዋሃደ። 3. ተጋባ፣ በጋብቻ ተሳሰረ፣ ተዋለደ ።

ተዛምዶ(ተዘምዶ) ስ ዝምድና ::

አዛመደ ግ 1. አወዳጀ፥ አስማማ። 2. አዋሃደ። 3. አገናዘበ፡ አመሳሰለ፥ አያያዘ፡ አገናኘ ።

አዛማጅ ቅ አገናኝ።

አዝማች ቅፅል ስ (ሰዋ.) መስተዋምር "የ" በሃላፊ አንቀፅ ላይ እያረፈ ግሱን ከስም ጋር የሚያዛምድ ምእላድ፤ መስተፃምራዊ ቅስልም ይባላል (ለምሳሌ፡ የገባ ያገለግላል በሚለው አነጋገር ውስጥ "የ" አዛማጅ ቅፅል ነው። በአሁንና በትንቢት ጊዜያት ደግሞ "የም" ወይም "የሚ" ይሆናል። የምትናገረውን አስበህ ተናገር በሚለው ውስጥ "የም" አዛማጅ ቅፅል ነው)።

ዘማሪ "ዘመረ" ስር ተመ.

ዘማች "ዘመተ" ስር ተመ.

ዘማኑም ስ ጥንብ በላ የአሞራ አይነት።

ዘማዊ "ዘሞተ" ስር ተመ.

ዘምቢል "ዘንቢል" ን ተመ.

ዘምባባ "ዘንባባ" ን ተመ.

ዘምናና "*ዘበነነ" ስር **"ዘብናና"** ን ተመ.

ዘምዛሚ "ዘመዘመ" ስር ተመ.

ዘሞተ ግ ሴሰነ፥ አመነዘረ።

ዘማዊ ስ አመንዝራ፥ ሴሰኛ።

ዝሙት ስ ሴሰኝነት፥ ሽርሙጥና፥ አመንዝራነት።

ዝሙት አዳሪ ስ በሽርሙጥና የምትተዳደር ሴት፤ ሴተኛ አዳሪ።

ዝሙተኛ ቅ ዘማዊ፤ አመንዝራ።

ዘረመትራን(ዘረመትር) ስ የአሳ መያዣ ወጥመድ፤ መግለቢ።

ዘረመጠ ግ በሃይል ወጋ፥ ቀረቀረ፥ ከተተ፥ ዶለ (ጦር፥ ጋሬጣ፥...)።

ዘረምቦ "ዘረንቦ"ን ተመ.

ዘረረ ግ 1. ዘረጋ፡ አሰጣ። 2. አጋደመ። 3.ጣለ፥ ደበለለ።

ተዘረረ ግ 1. ተዘረጋ፤ ተሰጣ። 2. ተጋደመ፥ ወደቀ፥ተኛ።

ዘረር ስ ለናፍጭ የሚመስል፤ በየማሳው ውስጥ በቅሉ የሚገኝ የጎመን አይነት፤ ወፍ ዘረር እየተባለም ይጠራል።

ዘረ ቆርጥም "ዘራ" ስር ተመ.

***ዘረበረበ**

ተዝረበረበ ግ ተንጠባጠበ (ለሃጭ)።

አዝረበረበ ግ አንጠባጠበ።

***ዘረበበ**

ተንዘረበበ ግ ተንጠለጠለ፥ ተንዘለዘለ፥ ወደ ታች ወረደ (ከንፈር)።

አንዘረበበ ግ አንጠለጠለ፥ አንዘለዘለ፥ ወደታች አወረደ(ከንፈርን)።

ዘረ ቢስ "ዘራ" ስር ተመ.

ዘረነቀ ግ 1. አሰቦታው፡ አለአግባቡ አስገባ፡ ዶለ፡ ጨመረ። 2. ዘባረቀ፥ ነገር አበላሸ።

ዘረንቦ (ዘረምቦ) ስ እድሜው አነስተኛ የሆነ ከጫጩት ከፍ የሚል ዶሮ።

ዘረኛ "ዘራ" ስር ተመ.

ዘረኝነት ዝ.ከ

ዘረ አዳም ዝ.ከ

***ዘረከረከ**

ዘረክራካ (ዝርክርክ) ቅ ጥንቁቅ ያልሆነ፥ ጥንቃቄ፥ ብቃት፥ ጥራት፥... የሚያንሰው።

ዝርክራኪ ቅ የተንጠባጠበ፤ ሙድቅዷቂ።

ዝርክርክ አለ ግ ተዝረከረከ።

ዝርክርክ አደረገ ግ አዝረከረከ።

ተዝረከረከ ግ 1. ተንጠባጠበ፥ እዚህም እዚያም ተበታተነ። 2. ፅዳት የጎደለው ሆነ፡ በመልክ በመልኩ ያልተሰናዳ ሆነ፡ ምስቅልቅል አለ። 3. ሳይሰበሰብ፡ ሳይከናወን፥ሳይጠናቀቅ ቀረ። 4. ተጎሰጎሰ፥ ወጣ፥ ተነገረ(ምስጢሩ)።

አዝረከረከ ግ 1. አንጠባጠበ፡ በታተነ። 2. ያለ ጥንቃቄ አደረገ፥ ሰራ፥...። 3. እዚህም እዚያም ምስቅልቅል አደረገ። 4. ሳይሰበሰብ፥ ሳያከናውን፡ ሳያጠናቅቅ ቀረ። 5. ጎሰጎሰ፥ አወጣ፡ ተናገረ(ምስጢርን)።

ዘረክቦ ቅ ቀፈታም፥ ሆደ ዘርጣጣ።

ዘረከተ ግ ቀደደ፥ በሸረከ፥ ሸረከተ።

ተዘረከተ ግ ተቀደደ፡ ተሸረከተ።

ዘረክራካ "*ዘረከረከ" ስር ተመ.

ዘረዘረ ግ 1. እንደ ገብስ፥ ስንዴ፥ በቆሎ፥ ዘንጋዳ፥... የመሳሰለው ሁቃያ አድጎ ማሸት ወይም ማፍራት ጀመረ። 2. ሸከሸከ፡ ትቅጥቅ እንዳይል አደረገ (ለምሳሌ ሸማኔ ሸማን)። 3. ነጣጠለ፥ ለያየ፡ በተንተን አደረገ። 4. ጥርሱ ሳለቀ ማሳድ ጥርስ አበጀ፥ ሞረደ። 5. ጥቅል ገንዘብን ወደ አነስተኛ ክፍልፋይ ወይም ሽርፍራፊ ገንዘብ ቀየረ፡ ለወጠ፡ መነዘረ። 6. አልፎ አልፎ ሽበት ጣል ጣል አደረገበት፥ ገብስማ ሆነ (ፀጉር)። 7. ተነተነ፥ ዝርዝር አወጣ፥ ጥቅል የነበረውን አፍታታ።

ዘረዘረች ግ ባል ሳታገባ ጊዜው አለፈበት፥ ቆማ ቀረች(ልጃገረድ)።

መዘራዝር ስ ስራው ሲያልቅ ትንሽ የቀረውና ከፊት ግንድ አካባቢ የደረሰ የሸማ ድር እንድነት እጅብ እያለ ለአሰራር እንዳያስቸግር ሸማኔው ድሩን በክፍል በክፍል እየመደበ የሚያበጀው ቋጠሮ፥ ቁጥረት።

መዘራዝር ገባ ተሰርቶ ሲያልቅ ደረሰ (ሸማ)።

መዘርዝር ስ ሪፖርት፥ ዘገባ።

ዘርዛራ ቅ ያልተጠጋጋ፤ በየመሃሉ ሰፋ ሰፋ ያለ ክፍተት ያለው (ማጭድ፥ ወንፊት፥ ጥርስ፥...)።

ዘርዛራ ወንፊት (ዘይ.) ምስጢር የማይደብቅ፥ ወሬኛ።

ዝርዝር ስ 1. የጥቅል ገንዘብ ክፍልፋይ፤ ምንዛሪ፤ ሽርፍራፊ። 2. እያንዳንዱ ስም፤ እቃ፥...የተመዘገበበት ፅሁፍ። ቅ 3. በተናጠል ያለ ወይም የተቀመጠ እያንዳንዱ (ነገር)። 4. በዶሮ ጭንቅላት ላይ እንደ ቁንጮ ሆኖ የሚበቅል ስስና ነጠላ ቀጸ፥ ዱልዱም ያልሆነ። *ዝርዝር ዶሮ*። 5. ጥቅጥቅ ያልሆነ፤ የተበታተነ።

በዝርዝር አንድ ባንድ፥ በስፋት። *ዜናውን በዝርዝር ነገረኝ*።

ዝርዝር ውስጥ ገባ ስለእያንዳንዱ ጉዳይ በስፋትና በጥልቀት ተናገረ ።

ዝርዝር እርባታ ስ (ሰዋ.) ግስንና ስምን በተለያዩ መደቦች፤ ፆታና ቁጥር (እኔ፥ አንተ፥ አንቺ፤ እኛ፥...) የመተንተን ተግባር።

ተዘረዘረ ግ 1. አንድ ባንድ ተተነተነ፥ ተነገረ፥ ተጠቀሰ። 2. ወደ ቅንስናሽ ገንዘብ ተለወጠ፤ ተመነዘረ (ጥቅሉ ገንዘብ)። 3. ተራራቀ፤ በተን በተን አለ፤ ሳይጠቀጠቅ፥ ሳይጠጋጋ ቀረ።

ተዘራዘረ ግ ተሰዳደበ፤ አንዱ የሌላውን ጉድ አወጣ።

አዘረዘረ ግ 1. ማፍራት፥ ፍሬ መያዝ ጀመረ። 2. ሸበተ፥ ገብስማ ሆነ (ፀጉር)። 3. መነዘረ።

*ዘረዘረ

ተንዘረዘረ ግ ተንቀጠቀጠ (በእልህ፥ በቁጣ፥ በህመም፥...)።

አንዘረዘረ ግ አንቀጠቀጠ (እልህ፤ ቁጣ፥ ህመም)።

ዘረገፈ ግ 1. ዘከዘከ፥ ጎለጎለ (ከውስጥ)። 2. ደፋ፥ ገለበጠ፥ አራገፈ። 3. አወጣ፤ ዘረዘረ (ምስጢርን)።

ዘርጋፋ ቅ (ዘይ.) በርጫም፥ ሆደ ትልቅ።

ዝርግፍ ዝ.ከ.

ዝርግፍ ወርቅ ስ ከወርቅ የተሰራ የአንገት ጌጥ አይነት።

ዝርግፍግፍ ወጣ 1. ተዘረገፈ፤ ተበታተነ። 2. ተገለጎለ። 3. (ዘይ.) ገዘፈ፥ ወፈረ (ሰውነቱ)።

ተዘረገፈ ግ 1. ተዘከዘከ፥ ተጎለጎለ። 2. ተደፋ፤ ተገለበጠ፤ ተበተነ። 3. በርጭ አወጣ፤ በጣም ወፈረ።

ዘረጋ ግ 1. አጋደመ፥ አንጋለለ፥ አስተኛ። 2. ቀጥ አደረገ፥ አረዘመ። *በጣቶቹ ኮርኒሱን ለመንካት እጁን ዘረጋ/ዛፉ ቅርንጫፎችን በሰፊው ዘረጋ*። 3 ከፈተ፥ ገለጠ። *መፅሃፉን ዘረጋ*፡ 4. ወጠረ። *ዝናብ እንዳይመታው ጥላውን ዘረጋ* ። 5. ቀጥ አደረገ፤ አቃና፥ አስተካከለ (የተጣጠፈን፤ የተጨበጠን፤ የተጠማዘዘን፥ የተኮማተረን፥ የጎረበን፥...)። 6. አሰጣ፥ አነጠፈ፥ ዘረረ። *የታጠበውን ልብስ ከሽቦው ላይ ዘረጋ/ ምንጣፉን ከወለሉ ላይ ዘረጋ*። 7. ፈታ፥ ተረተረ (የተጠቀለለን)። 8. ጣለ፤ ዘረረ (በዱላ፥ በጥይት፥...)። 9. አቋቋመ፤ አበጀ፤ መሰረተ። *የልማት አውታሮችን ዘረጋ*፡

ዝርግ ቅ 1. የተዘረጋ፤ ሰፋፋ፥ ጠፍጣፋ የሆነ። 2. (ስድብ) ስራፊት፥ ሰነፍ።

ዝርግ ሳህን ስ ሰፋፋ የሆነ ወይም ጎድጓዳነት የሌለው የመመገቢያ ሳህን።

ዝርግት አለ ግ ወደቀ (በህመም፥ በሞት፥...)።

ተዘረጋ ግ 1. ተጋደመ፤ ተኛ። 2. ተወጠረ፥ ተገተረ። 3. ቀና፥ ቀጥ አለ፤ ተስተካከለ። 4. ተመሰረተ፥ ተቋቋመ፥ ተዘጋጀ ።

ተዘረጋጋ ግ አቅም አጣ፥ ተዝለፈለፈ፥ ዢ ብሎ ተኛ።

ተንዘራጋ ግ ዢ ብሎ ወደቀ።

አንዘራጋ ግ ክፉኛ ጣለ (በሽታ ሰውን)።

*ዘረጠ

ዘረጦ ቅ 1. (ስድብ) ፈሳም። 2. ፈሪ፥ ቡከን። 3. ስራፊት፥ አውደልዳይ።

ዘርጣ ቅ አፉ እንዳመጣለት የሚናገር፥ ተሳዳቢ፥ ምላሰኛ። *ለፈ ዘርጣ* ።

ዘረጥ አለ ግ የፈስ ድምፅ ተሰማ።

ዘረጥ አደረገ ግ የፈስ ድምፅ አሰማ።

ዘረጥራጣ(ዝርጥርጥ) ቅ 1. (ስድብ) ፈሳም፤ ፈሱን እንደ አህያ የሚያጮህ። 2. ፈሪ፥ ቡከን።

ተዝረጠረጠ ግ ተንበቀበቀ፥ ፈስ በፈስ ሆነ።

አዘረጠ ግ ፈሱን እንደ አህያ ዘረጥ አደረገ፥ የፈስ ድምፅ አሰማ።

አዝረጠረጠ ግ 1. አምበቀበቀ፥ አከታተሎ የፈስ ድምፅ አሰማ፥ አጮሀ። 2. አስጨነቀ፥ አርበደበደ። 3. ጉድ አስወጣ፥ አስጎለጎለ።

አንዛረጠ ግ 1. እንደ አህያ ፈሳ፤ ፈሱን አጮሀ፥ አሰማ። 2. አዘጠዘጠ፥ ስራ ፈታ፥ አውደለደለ።

አንዛራጭ ቅ ስራ ፈት፥ አውደልዳይ።

ዘረጠጠ ግ 1. እግርን ሳበ፣ ጎተተ (ለመጣል)። 2. በጥርሱ ዘነጠለ፣ ቦተረፈ፣ ዘረገፈ፣ ጣለ። *ጅቡ ላሀያዋን ዘረጠጣት* ። 3. ናደ፣ አፈረሰ፣ ዘረገፈ (ክምርን)። 4. ክፈት ክፈት አደረገ፣ አራራቀ። 5. ለአንድ ሰው የሚገባውን ክብር ነሳ፣ አዋረደ (በመጥፎ አነጋገር)።

ዘርጣጣ(ዘረጠጥ) ቅ (ስድብ) ቀብዳዳ፣ ቀፈታም፣ በርጫም።

ዝርጥጥ ዝ.ክ.

ዝርጥጥ አለ ግ 1. ክስሩ ሰፋ ያለ ሆነ። *የእህሉ ክምር ዝርጥጥ ብሏል*። 2. ተንዘረጠጠ።

ተዘረጠጠ ግ ተናደ፣ ፈረሰ (ክምር)።

ተንዘረጠጠ ግ ተንቀበደደ፣ ተንገፈጠጠ፣ በርጫም ሆነ።

አንዘረጠጠ ግ አንገፈጠጠ (ሆድን)።

ዘረጥራጣ "*ዘረጠ" ስር ተመ.

ዘረጦ ዝ.ክ.

ዘረፈ ግ 1. ቀማ፣ ነጠቀ፣ ወሰደ (የሌላውን ንብረት)። 2. ጊዜ ሳይፈጅበት በአንድ አፍታ ቅኔ አቀነባብሮ (አሳክቶ) አቀረበ፣ አሰማ፣ ተናገረ። 3. በጣም በርካሽ ገዛ።

ዘረፋ ስ 1. የሌላን ንብረት በሃይል መውሰድ፣ ቅሚያ፣ ንጥቂያ። 2. ጊዜ ሳይፈጅ በፍጥነት እየተቀነባበረ በቃል የሚነገር የቅኔ አደራረስ። 3. የርካሽ ግዢ።

ዘራፊ ስ 1. ቀማኛ፣ ወንበዴ፣ ነጣቂ። 2. ጊዜ ሳይፈጅበት፣ ወዲያው ወዲያው ቅኔ የማቀናበር፣ የማዘጋጀት፣ የማፍሰስ ችሎታ ያለው (ለቅኔ ተማሪ)።

ዘራፍ ስ 1. ጀግንነትን፣ ልበሙሉነትን፣ ድፍረትን፣ ቆራጥነትን፣ አልበገር ባይነትን፣... በማስመልከት፣ ክፍ ባለ ድምፅ የሚባል ፉከራ፣ የፉከራ አዝማች፣ የድንፋታ ቃል። ቅ 2. ቸር፣ ለጋስ፣ ሲሰጥ እጁ የማይሰሳ። *እገሌ እጁ ዘራፍ ነው*።

ዘራፍ አለ 1. ተቆጣ፣ ደነፋ፣ *እንዴት ይሆናል አለ*። 2. ፎከረ።

ዝርፊያ ስ ቅሚያ፣ ንጥቂያ።

ተዘረፈ ግ ተቀማ፣ ተነጠቀ፣ ንብረቱ ተወሰደበት።

***ዘረፈ**

ዘርፍ ስ 1. በጃንጥላ፣ በአልጋ ልብስ፣... ዳር ዳር ለጌጥ የሚሰራ መርገፍ። 2. ክፍል፣ ወገን። እጅ. *በኢኮኖሚው ዘርፍ ብዙ እርምጃዎች ተወስደዋል*። 3. (ሰዋ.) በአንድነት እንዲናበቡ ወይም እንዲጣመሩ በሚደረጉ ቃላት ውስጥ "የ" የሚያርፍበት ቃል ምጠሪያ። (ለምሳሌ የቤት ልጅ፣ የእንጀራ እናት፣ ቤተክርስቲያን (የክርስቲያን ቤት) በሚሉት ሃረጎች ውስጥ፣ ልጅ የቤት፣ እናት የእንጀራ፣ ክርስቲያን ደግሞ የቤት ዘርፍ ናቸው)።

ዘረፍራፋ ቅ 1. ዘርፍ ያለው። 2. ዝርክርክ።

ተዛረፈ ግ ሁለት ወይም ከሁለት የበለጡ ቃላት ተጣምረው የአንድ ቃል መልክ እንዲይዙና በአንድነት እንዲነበቡ ተደረገ፣ ተያያዘ፣ ተጣመረ (ቃልና ቃል)።

ተዝረፈረፈ ግ 1. ዘርፉ በዛ፣ ረዘመ። 2. ተዘናፈለ (ፀጉር)። 3. ተዝረከረከ።

አዛረፈ ግ (ሰዋ.) ቃልና ቃልን አጣመረ፣ አናበበ፣ አያያዘ፣ ዘርፍና ባለቤት አደረገ።

አዝረፈረፈ ግ አዝረከረከ፣ አበላሸ።

***ዘረፈጠ**

ዘረፈጥ (ዘርፋጣ) ቅ (ስድብ) ከተቀመጠበት የማይነሳ፣ ሰነፍ፣ ረሀጥ፣ ስራ የማይችል፣ ገልቱ።

ዝርፍጥ ዝ.ክ.

ተዘረፈጠ ግ በስንፍና ወይም በግዴለሽነት እግሩን ዘርግቶ ተቀመጠ።

ተንዘራፈጠ ግ ተመቻችቶ፣ ተደላድሎ፣ እንደልቡ ተቀመጠ።

አንዘራፈጠ ግ አመቻችቶ፣ አደላድሎ አስቀመጠ።

***ዘረፈፈ**

ዘረፈፍ (ዘርፋፋ) ቅ 1. ከርፋፋ፣ ቀርፋፋ። 2. በጣም ረዥም በመሆኑ መሬት ሊነካ የደረሰ (ለምሳሌ ልብስ፣ የዛፍ ቅርንጫፍ)።

ዝርፍፍ አለ ግ ተንዘረፈፈ።

ዝርፍፍ አደረገ ግ አንዘረፈፈ።

ተንዘረፈፈ ግ 1. አለቅጥ ረዘመ (ለምሳሌ ልብስ፣ መጋረጃ)። 2. ተንቀረፈፈ፣ ተንቀረደደ፣ ተጎተተ።

አንዘረፈፈ ግ 1. አለቅጥ አስረዘመ (ለምሳሌ ልብሱን)። 2. አንቀረፈፈ፣ ጎተተ።

ዘረፋ "ዘረፈ" ስር ተመ.

ዘረፍራፋ "*ዘረፈ" ስር ተመ.

ዘራ ግ 1. እንዲበቅል በመሬት ላይ በተነ፣ ረጨ፣ ነሰነሰ (ዘርን)። 2. ነዛ፣ አዳረሰ፣ ናኘ (ወሬን፣ በሽታን)። 3. (ዘይ.) በተነ፣ አባከነ (ገንዘብን)።

^{1}**ዘር** ስ 1. ሲዘሩት የሚበቅል ፍሬ (የእፅዋት፣ የእህል፣...)። 2. ልጅ (የሰው፣ የእንስሳ)። 3. ወገን፣ ዘመድ፣ ትውልድ፣ ተወላጅ። 4. በግብረ ስጋ ግንኙነት ጊዜ ከወንዱ አባለ ዘር የሚወጣው ፈሳሽ። 5 የፊደላት ቅርፅ ወይም መልክ። *ልጁ የፊደላትን ዘር በሚገባ ለይቷል*።

ዘር ቆጠረ የትውልድ ሃረግን ተነተነ፣ ዘረዘረ።

ዘር ተካ ወለደ።

ዘር ይመስክር ክፉም ሆነ ደግ የወላጅ የስራ ውጤት በልጅ ላይ ይታይ (በልጅ መባረክ ወይም መረገም ይገለፅ)።

ዘር ይውጣልህ (ምር.) ዘርህ፣ ትውልድህ ይባረክ፣ ደህና ልጆች ይብቀሉበት።

ዘርህ ይለምልም (ምር.) ዘርህ ይባረክ፣ ይበርክት ፡ ይብዛ።

ዘረቆርጥም ቅ 1. የዘሩበትን የማያበቅል (መሬት)። 2. የተማረውን ትምህርት በቶሎ የሚረሳ (ሰው)። 3. የተማረውን ለሌላ ሳያስተምር የቀረ (ምሁር)።

ዘረቢስ ቅ (የን.እን.) የመጣበት የማይታወቅ።

ዘረአዳም ስ (ኢ.አ.ተ.ቤ.) 1. ለኔቢጤ ወይም ሰባይተዋር በነፃ የሚደረግ አጠር ያለ የፀሎተ ፍትሃት አይነት።2. የሰው ዘር።

ዘር ማንዘር (ዘራንዘር) ስ የአንድ ነገር ዝርያ በአጠቃላይ።

የዘር ሃረግ ስ የዘር፣ የትውልድ አመጣጥ፣ ተዛምዶ።

የዘር ልዩነት ስ አንዱን የሰው ዘር በመደገፍና ከፍ ከፍ በማድረግ ሌላውን ዘር የማግለል፣ የመጫን፣ የመለየት፣ የመጨቆን ድርጊት።

የዘር መድልዎ ስ በዘር ላይ ተመስርቶ በሰዎች ላይ የሚደረግ አድልዎ፣ ተፅእኖ።

የዘር ወራት ስ ዘር የሚዘራበት ወቅት።

የዘር ግንድ ስ የአንድ ቤተሰብ ወይም ተወላጆች ከስር ተያይዞ የመጣ ዋነኛው መስመር (የዘር አባት ወይም እናት)።

ዘረኛ ቅ ሰዎችን በዘር ከፋፍሎ የሚያጋጭና በዘር ምክንያት ለአንዱ እያደላ ሌላውን የሚጎዳ፣ የዘረኝነት አስተሳሰብን፣ አመለካከትን የሚያራምድ።

ዘረኝነት ስ የዘር ልዩነት፤ በዘር መድልዎ ላይ የተመሰረተ አስተምህሮ፣ ፖሊሲ፣ አመለካከት።

ዝሪት ስ ተዘርቶ የበቀለ የእህል ቡቃያ።

ዝር ስ በማሳ ላይ የተዘራ፣ የተበተነ እህል።

ዝርያ ስ 1. ዘመድ፣ ወገን፣ ነገድ፣ ተወላጅ። 2. አይነት።

ተዘራ ግ 1. በእርሻ ላይ ተበተነ፣ ተረጨ (ዘር)። 2. ተሰራጨ፣ ተራባ።

አዘራ ግ የእህልን ፍሬ ከገለባ ወይም ከእብቅ ለመለየት ወደላይ እየበተነ አነፈሰ፣ ለንፋስ ሰጠ።

አዘራች ሽል ያዘች፣ አረገዘች (ላም)።

ዘራፊ "ዘረፈ" ስር ተመ.

ዘራፍ ዝ.ክ.

ዘር "ዘራ" ስር ተመ.

ዘርማንዘር ዝ.ክ.

ዘርዛራ "ዘረዘረ" ስር ተመ.

ዘርጋፋ "ዘረገፈ" ስር ተመ.

ዘርጣ "ዘረጠ" ስር ተመ.

ዘርጣጣ "*ዘረጠጠ" ስር ተመ.

ዘርጭ እንቧይ ስ ቁመቱ አስተናግር የሚያህል፣ አተር የሚያክሉ ፍሬዎች ያሉት፣ ግንዱና ቅጠሉ ላይ እሾህ ያለበት የእፅዋት አይነት።

ዘርፋጣ "ዘረፈጠ" ስር ተመ.

ዘርፋፋ "ዘረፈፈ" ስር ተመ.

ዘርፍ "*ዘረፈ" ስር ተመ.

ዘቀዘቀ ግ 1. የላዩን ወደ ታች አደረገ፣ ገለበጠ፣ ደፋ። 2. ጋዳላ፣ ዘንባላ፣ ቀልቋላ እንዲሆን አደረገ። 3. ጋዳላ፣ ዘንባላ ሆነ፣ አቆለቆለ። 4. ወደ ታች ወረደ፣ አመራ፣ ተጓዘ።

ዘቅዛቃ ቅ 1. ዘንባላ፣ ጋዳላ፣ ቀልቋላ። 2. ተዳፋት፣ ቁልቁለት (መንገድ)።

ዝቅዝቅ ቅ 1. ቁልቁል። 2. ጥለቱ ወይም መቋጫው እንደቀሚስ ጥለት በእግር አቅጣጫ እንዲሆን ተደርጎ የተዘጋጀ (ጋቢ፣ ኩታ)።

ተዘቀዘቀ ግ 1. ከወደ ላይ በኩል የነበረው ወይም ከላይ መሆን የነበረበት ወደታች በኩል ሆነ። 2. ከራሱ በኩል ወደ ታች፣ ከእግሩ በኩል ወደ ላይ ሆነ።

አዘቀዘቀ ግ አቆለቆለ፣ ወደ ታች ወረደ፣ ሄደ።

አዘቀዘቀች በግርጌ በኩል የሚውለውን የነጠላ ጫፍ በራስጌ በኩል አድርጋ ለበሰች፤ አሸረጠች (በሃዘን ምክንያት)፤ ዘቅዝቃለችም ይባላል።

ዘቀጠ ግ 1. ሰመጠ፣ ዘገጠ፣ ወደ ስር ወረደ (በፈሳሽ ውስጥ)። 2. ሰረገ፣ ወደ መሬት ውስጥ ገባ፣ ተቀመጠ (ፈሳሽ)። 3. (ዘይ.) በአስተሳሰቡ፣ በአደራረጉ ብልሹ፣ አጥፊ ሆኖ ተገኘ፣ አሽቆለቆለ ወራዳ ሆነ።

ዝቃጭ ስ ከፈሳሽ ስር ተኝቶ የሚገኝ እንደ አተላ ያለ አሰር፣ ቆሻሻ።

ዝቃጫም ቅ (ስድብ) ቆሻሻ።

ዝቅጥቃጭ ስ በብዛቱም ሆነ በአይነቱ በርከት ያለ ዝቃጭ።

አዘቀጠ ግ ዘቀጠ።

ዘቃቅቤ (ዝቃቅቤ) ስ በቅመምነት የሚያገለግል አነስተኛ ተክል፤ በሶብላ።

ዘቅዛቃ "ዘቀዘቀ" ስር ተመ.

ዘበለለ ግ ትልቅና ደንዳና የሆነ አይነ ምድር አወጣ፣ ተፀዳዳ።

ዘበተ ግ 1. ተሳለቀ፥ ቀለደ፥ አላገጠ፥ አሽሟጠጠ። 2. ዛተ፥ ፎከረ፥ አስፈራራ።

መዘበቻ ስ መሳለቂያ፥ መቀለጃ፥ መተረቻ።

ዘበት ስ ቀልድ፥ ለግጥ፥ ፌዝ፥ ቧልት።

ዘበት ነው ቀልድ ነው፤ አይሆንም፥ አይደረግም።

ዝብብት ስ ስላቅ፥ ሽሙጥ፥ ፌዝ፥ ቧልት።

ተዘባበተ ግ ተሳለቀ፥ ቀለደ፥ አሾፈ፥ አፌዘ።

መዘባበቻ ስ 1. መቀለጃ፤ ማሾፊያ፤ መተረቻ። 2. መዛቻ፥ መፎካከሪያ።

ዘበተረ ግ በጨቀ፥ በተረፈ፥ ዘንተረ።

ዘበት "ዘበተ" ስር ተመ.

ዘበነ "ዘመነ"ን ተመ.

***ዘበነነ**

ዘብናና (ዘምናና) ቅ ኩራተኛ፥ ቀብራራ።

ዝብንን አለ ግ ተዘባነነ።

ዝብንን አደረገ ግ አዘባነነ።

ተዘባነነ ግ ተኩራራ፥ ተንቀባረረ።

ተዘባናኝ ቅ ኩራተኛ።

አዘባነነ ግ አኩራራ፥ አንቀባረረ።

ዘበናይ "ዘመነ" ስር "ዘመናይ"ን ተመ.

ዘበኛ "ዘብ" ስር ተመ.

ዘበዘበ ግ 1. ነተረከ፤ ነዘነዘ፤ ጨቀጨቀ። 2. ነገር አስረዘመ፥ አንዛዛ።

ዘብዛባ ቅ ነትራካ፤ ነዝናዛ፤ ጨቅጫቃ። 2. ነገር ቶሎ የማይቆርጥ።

ዘበጠ ግ 1. መታ (በዱላ)። 2. ተለመጠ፥ ጎበጠ። 3 ጎደጎደ (መሬት)።

ዘባጣ ቅ 1. ጎባጣ፥ ለማጣ። 2. የጎደጎደ፥ ረባዳ (መሬት)።

ዘብጥ ዝ.ክ.

ተዘበጠ ግ ተመታ።

አዘበጠ ግ 1. ዘባጣ አደረገ። 2. ዘበጠ።

ዘበጣጥ (ዘብጣጣ) ቅ (ስድብ) ቂጣም።

ዘቢብ ስ የደረቀ የወይን ፍሬ።

ዘባ ግ ጎበጥ አለ፥ ተለመጠ፥ ተጣመመ።

ተዛባ ግ 1. ጎበጥ አለ፤ ተዛነፈ፥ መስመሩን ለቀቀ። 2. ተሳሳተ፥ ተጣመመ።

አዛባ ግ 1. አዛነፈ፤ መስመሩን እንዲለቅ አደረገ። 2. አሳሳተ፥ አጣመመ። *ነገሩን አዛብቶ አቀረበ።*

ዘባረቀ ግ 1. አምታታ፥ ደባለቀ፥ አባባተ (ሃሳብን ወይም ሌላ ነገርን)። 2. የሆነ ያልሆነውን ተናገረ።

ዘባራቂ ቅ አምታች፤ ነገር የሚያባክር፥ እንደመጣለት የሚለፈልፍ።

ተዘባረቀ ግ ተደባለቀ፤ ተቀላቀለ፤ ተምታታ።

ተዘበራረቀ ግ ተደበላለቀ፤ ተመሰቃቀለ፤ ተምታታ፥ ግልፅነት አጣ።

አዘባረቀ ግ አምታታ፥ አደባለቀ፥ ስርአት አሳጣ።

አዘበራረቀ ግ አመሰቃቀለ፥ አደበላለቀ፥ አምታታ።

ዘባተሎ ስ ቡትቶ፥ የተቀዳደደ ልብስ።

ዘባተሏም ቅ (የን. አነ.) ዘባተሎ የሚለብስ፥ ቡቱቷም።

ዘባጣ "ዘበጠ" ስር ተመ.

ዘብ ስ በጥበቃ ስራ ላይ የተመደበ ሰው።

ዘብ ቆመ በጥበቃ ስራ ላይ ሆነ፤ ተሰማራ።

ዘብ ጠባቂ ስ ዘበኛ።

ዘበኛ ስ መስሪያ ቤቶችን ወይም የግለሰቦችን ቤትና ንብረት የሚጠብቅ ሰው።

ዘብናና "ዘበነነ" ስር ተመ.

ዘብዛባ "ዘበዘበ" ስር ተመ.

ዘብጣጣ "ዘበጣጥ"ን ተመ.

ዘብጥ "ዘበጠ" ስር ተመ.

ዘብጥያ ስ እስር ቤት።

ዘብጥያ ወረደ እስር ቤት ገባ፤ ታሰረ።

***ዘቦጠቦጠ**

ዝቡጥቡጥ ቅ 1. የወፈረ፥ የደፈረሰ፥ ያልጠራ (ጠላ ወይም ፈሳሽነት ያለው ነገር)። 2. ጓጓላ ያለበት፥ በወጉ ያልተበጠበጠ (ለምሳሌ ተልባ)። 3. በሚያስጠላ ሁኔታ የወፈረ (ሰው)።

ዝቡጥቡጥ አለ ግ ተዝቦጠቦጠ።

ዝቡጥቡጥ አደረገ ግ አዝቦጠቦጠ።

ተዝቦጠቦጠ ግ 1. በወፍራሙ ተበጠበጠ፤ ጓጓላ ሆነ። 2. ያለ ልክ ወፈረ።

አዝቦጠቦጠ ግ በወፍራሙ በጠበጠ፤ አጓጎለ። 2. ያለ ልክ አወፈረ።

ዘቸ

ዘቸ ዘቸ አለ ግ ሮጥ ሮጥ፥ ዞጭ ዞጭ አለ (የወፍራም ሰው አሯሯጥ)።

ዘነቀ ግ ቀየጠ፥ ቀላቀለ፥ ደባለቀ፥ ጨመረ።

ዝንቅ ቅ ቅይጥ፥ ድብልቅ፥ ቅልቅል።

ዝንቅ ኢኮኖሚ ስ ቅይጥ ኢኮኖሚ።

ተዘነቀ ግ ተቀላቀለ፥ ተቀየጠ፤ ተደባለቀ።

ተዛነቀ ዝ.ክ.

አዛነቀ ግ አደባለቀ፥ አቀያየጠ።

ዘንቆለ ግ ወጋ፥ ጠንቆለ፥ ደንቆለ።

ዘንቁል ቅ የነገር ስልት የማያውቅ፥ ዘባራቂ፥ ነገር የሚያበላሽ።

ዘነበ (ዘነመ) ግ ከሰማይ፥ ከዳመና ውስጥ ዝናብ ወረደ፥ ወደ መሬት ተንጠባጠበ።

ዘነበለት አገኘ (ገንዘብ)።

ዝናብ (ዝናም) ስ ከላይ፥ ከሰማይ፥ ከዳመና ወደ መሬት የሚወርድ የውሃ ነጠብጣብ።

ዝናቡን ለግቷል በቂ ዝናብ ዘንቧል።

ዝናቡን ቀዳው በጣም ዘነበ።

ዝናብ መታው / ደበደበው ዝናብ አበሰበሰው፥ ዘነበበት።

ዝናብ ጣለ ዝናብ ዘነበ።

የዝናብ ልብስ ስ ውሃ የማያስገባ፥ በዝናብ ጊዜ የሚለበስ ልብስ።

ዝናባማ ቅ ዝናብ የሚበዛበት፥ ብዙ ጊዜ የሚዘንብበት (ቦታ፥ አካባቢ፥ ሃገር፥ ...)።

አዘነበ ግ 1. ዝናብ እንዲጥል አደረገ። 2. (ዘይ.) አዥጎደጎደ (ስድብን፥ ...)።

***ዘነበለ**

ዘንባላ ቅ ወደ አንድ ወገን ጋደል፥ ዘመም ያለ።

ዝንባሌ ስ 1. አዝማሚያ። 2. ምርጫ፥ ፍላጎት። *የስነ ፅሁፍ ዝንባሌ ላለው።*

ዘንበል አለ ግ 1. ወደ አንድ ወገን ዘመም፥ ጋደል አለ። 2. ወደ አንድ ወገን አደላ።

ዘንበል አደረገ ግ ጋደል፥ ዘመም አደረገ።

አዘነበለ ግ 1. አጋደለ፥ አዘመመ። 2. አደላ (የፍላጎት፥ የምርጫ)።

ዘነተረ ግ ቦጨቀ፥ ቦተረፈ።

ተዘነተረ ግ ተቦጨቀ፥ ተቦተረፈ።

***ዘነከተ**

ዘንካታ ቅ ያማረ፥ ውብ፥ መለሎ።

ተዘናከተ ግ ተዋበ፥ አማረ (በአረማመድ፥...)።

ዘነዘነ ግ ከፋፈለ፥ ሸነሸነ፥ አደላደለ።

ዝንዘና ስ ሽንሸና፥ ድልደላ።

ተዘናዘነ ግ ተከፋፈለ።

አዘናዘነ ግ ሸነሸነ፥ አከፋፈለ።

ዘነዘና^{1} ስ ከወፍራም እንጨት ወይም ከብረት የተሰራ መውቀጫ፤ የሙቀጫ ግልገል (ስእሉን ሙቀጫ ስር ተመ.)።።

ዘነዘና^{2} ስ 1.ውስጡ ክፍት የሆነ የእፅዋት አይነት። 2. ከዘነዘና እንጨት የሚሰራ ውኸም፤ የጋያ ጢስ መማጊያ።

ዘነጋ ግ ረሳ፥ ሳያስታውስ ቀረ።

ዝንጉ ቅ 1. የሚረሳ፥ የማያስታውስ። 2. ቸልተኛ፥ ተሳሳ።

ዝንጋታ ስ መርሳት።

ተዘነጋ ግ ተረሳ።

ተዘናጋ ግ ሳይጠነቀቅ ቀረ፥ ቸል አለ፥ ተሳነፈ።

አዘናጋ ግ 1. አረሳሳ፥ አታለለ። 2. አስረሳ።

አዘናጊ ቅ ሆን ብሎ የሚያረሳሳ።

አዘነጋ ግ አረሳሳ፥ አዘናጋ፥ አታለለ።

ዘነጠ ግ 1. ተሽቀረቀረ፥ አማረ፥ አጌጠ፥ ቆነጀ። 2. (ዘይ.) ተኩራራ።

ዘናጭ ቅ 1. አለባበሱን የሚያሳምር፥ ሽቅርቅር። 2. ጥሩ፥ ሸጋ።

አዘነጠ ግ አሽቀረቀረ፥ አስጌጠ፥ አሳመረ።

ዘነጠለ ግ 1. ቀደደ። 2. ገነጠለ፥ ከዋናው አካል ለየ። 3. ቦጨቀ፥ ቦተረፈ። *ጅብ የዘነጠለው ይመስላል።* 4. በዝንጥል መታ፥ ደበደበ። 5. ያነባበብን ስርአት እያበላሸ አነበበ። 6. (ዘይ.) አክብሮት ለሚገባው ሰው ተገቢውን አክብሮት ሳይሰጥ ቀረ (ለምሳሌ "እርስዎ" መባል የሚገባቸውን ሰው "አንተ" ወይም "አንቺ" እያለ አናገረ)።

ዝንጣይ ስ ጉንጣይ፤ የተገነጠለ የዛፍ ቅርንጫፍ ወይም የሌላ አካል ክፍል።

ዝንጥል ዝ.ከ.

ተዘነጠለ ግ 1. ተቀደደ፥ ተሸረከተ። 2. ተቦጨቀ፥ ተቦተረፈ። 3. ተዘነጠፈ፥ ተቆረጠ፥ ተገነጠለ። 4. በርጫም ሆነ፥ ሆዱ ተንቀበደደ።

ዘነጠፈ ግ ገነጠለ፥ ዘነጠለ፥ ቆረጠ፥ ቀጠፈ።

ዘንጣፋ ቅ ረዥም፥ ዠርጋዳ፥ ጥሩ አቋም ያለው።

ዝንጣፊ ቅ የተቆረጠ ቅርንጫፍ።

ተዘነጠፈ ግ 1. ወረደ፥ ዱብ አለ። 2. ተዘረረ፥ ወደቀ።

***ዘነፈ**

ዝንፈት ስ ተባለጥ፥ እላፊ፤ የሸማ ፈርጆች መበላለጥ፥ የንዱ ፈረጅ ርዝመት ከመንትያው ዝቅ ወይም ከፍ ብሎ መገኘት።

ዝንፍ እንዳትል 1. ከአካባቢው ዞር እንዳትል፥ እንዳትንቀሳቀስ፥ ወደሌላ አቅጣጫ እንዳትሄድ። 2. ቃልህን፥ ሃሳብህን፥... እንዳትቀይር።

ተዛነፈ ግ 1. ከመስመር ወጣ፥ ተዛባ፥ ተንጋደደ። 2. ተበላለጠ፥ አንዱ ከሌላው (ከአጣማሪው) ጋር ርዝመቱ ሳይመጣጠን ቀረ፥ ተረፈ (የነጠላ ወይም የጋቢ ፈርጅ)።

ተዛነፍ ስ ከፍና ዝቅ የማለት፡ ያለመስተካከል ሁኔታ።

አዛነፈ ግ 1. ከመስመር አወጣ፥ አዛባ፡ አንጋደደ፥ አወላገደ። 2. አበላለጠ፥ አንዱ ፈርጅ ከአጓዳኙ እንዲያንስ ወይም እንዲበልጥ አደረገ።

***ዘነፈለ**

ዘንፋላ ቅ 1. ውብና ለስላሳ የሆነ፥ የሚያምር (ለምሳሌ ፀጉር)። 2. አቋሙ የሚማርክ፥ በምቾት የተያዘ፥ ሸበላ፥ ዠርጋዳ።

ተዘናፈለ ግ 1. ረጅምና ለስላሳ ሆኖ አደገ (ፀጉር)። 2. በመጠኑ ጋደም፥ ዘንበል አለ (ለምሳሌ የተመቸውና ቁመናው ያማረ ሰብል)።

ዘና ግ 1. ረታ፥ ቀና፥ ተፍታታ፡ ተዘረጋጋ (ተኮራምቶ፥ ተጨማትሮ የነበረ አካል)። 2. ረጋ፡ አረፈ፥ ሃሳቡን ጣለ።

ዘና አለ ግ 1. ተዘናጋ። 2. ተመቻቸ፡ ተደላደለ፤ በድሎት ላይ ሆነ።

ተዛና ግ 1. ተፍታታ፥ ተዘረጋጋ። 2. ሃሳቡን ጣለ፥ ተደሰተ፤ እንደልቡ ሆነ፡ ተመቻቸ። 3. ቀበጠ፡ ተቀናጣ። 4. ተዘናጋ፥ ቸል አለ።

ተዝናና ግ 1. ተዛና፥ በልዩ ልዩ ነገር ራሱን አስደሰተ። 2. ሰውነቱን አፍታታ። 3. ተኩራራ። 4. ተቀናጣ፥ ቀበጠ።

መዝናኛ ስ የመደሰቻ፡ የማረፊያ ቦታ ወይም ጊዜ።

አዝናና ግ 1. በልዩ ልዩ ነገር አስደሰተ። 2. እንዲፍታታ፡ እንዲዘረጋጋ፥ እንዲመቻች፡ እንደልቡ እንዲሆን አደረገ።

አዝናኝ ቅ አስደሳች።

ዘናና ቅ ጭንቅላቱ ወይም ራሱ ትልቅ ሆኖ ወደ አንድ በኩል ዘንበል ያለ።

ዘናጭ "ዘነጠ" ስር ተመ.

ዘንቁል "ዘነቆለ" ስር ተመ.

ዘንቢል (ዘምቢል) ስ ከሰሌን ወይም ከቃጫ፥... የሚሰራና በእጅ የሚንጠለጠል የእቃ መያዣ።

ዘንባላ "ዘነበለ" ስር ተመ.

ዘንባባ (ዘምባባ) ስ የሰሌን ዛፍ አይነት።

ዘንች ስ ወደ ትልቅ ሬቅ ወይም ጎተራ ውስጥ ለመግባት ሲፈለግ በመረጋገጫነት እንዲያገለግል ተብሎ የሬቁን ወይም የጎተራውን ቁመት በማማከል አግድም የሚሰካ እንጨት።

ዘንካታ "ዘነከተ" ስር ተመ.

ዘንድ 1. ከስምና ተውላጠ ስም ጋር እየገባ ቦታን፥ በአጠገብ መገኘትን፥ ... የሚያመለክት ቃል። *መፅሃፉን እሱ ዘንድ ታገኘዋለህ/መፅሃፉ ከበደ ዘንድ ነው።* 2. በትንቢት አንቀፅ ከሚነገር ግስ ጋር እየገባ ግሱ እንዲያስር የሚያደርግ ቃል። *በዝግጅቱ ላይ ይገኝ ዘንድ ተጋብዞዋል።*

ዘንድሮ ይህ አመት፡ አሁን ያለንበት፡ የያዝነው አመት።

ዘንዶ ስ ርዝመቱና መጠኑ በጣም ትልቅ የሆነ የእባብ አይነት።

ዘንዶ

ዘንጋዳ ስ መጠኑና ቅርፁ ማሽላ የሚመስል የአገዳ እህል።

ዘንግ እንደምርኩዝ ወይም በትር ሆኖ የሚያገለግል ቀጠን፡ ረዘምና ቀጥ ያለ እንጨት ወይም ብረት።

ዘንጣፋ "ዘነጠፈ" ስር ተመ.

ዘንፋላ "*ዘነፈለ" ስር ተመ.

ዘከረ ግ 1. ሰጠ፥ መፀወተ። 2. በእግዚአብሔር፥ በፃድቃን፥... ስም ዝክር አዘጋጅቶ አበላ፡ አጠጣ። 3. የተዘጋጀውን ጠበል ጠዲቅ ፀሎት አድርጎ ባረከ። 4. አሰበ፥ አስታወሰ።

መዘከሪያ ስ ፀሎት እንዲደረግበትና እንዲባረክ ከዝክር ድግስ ላይ በትንሹ የሚወሰድ ጠበል ጠዲቅ።

ዝክር ስ በእግዚአብሔር፥ በፃድቃን፥... ስም የሚዘጋጅ ጠበል ጠዲቅ፡ ድግስ።

ተዘከረ ግ 1. ሰጠ፡ መፀወተ። 2. ታወሰ፥ ታሰበ። 3. የተዘጋጀው ጠዲቅ ፀሎት ተደረገበት ተቆረሰ።

ተዝካር ስ በሙታን ስም የሚዘጋጅ የመታሰቢያ ድግስ (ምግብና መጠጥ)።

ተዝካሩ ተበላ አለቀለት፥ አበቃ።

ተዝካሩ ወጣ 1. አለቀለት፥ አበቃ። 2. ለሞተ ሰው የአርባ ወይም የሰማንያ ቀን መታሰቢያ ተደገሰለት።

አዘከረ ግ ዝክር አደረገ፥ ደገሰ።

አዝካሪ ስ የዝክር ድግስ አዘጋጅቶ የሚያበላ፥ የሚያጠጣ ሰው።

ዘከዘከ ግ 1. ዘረገፈ፤ አራገፈ፥ ገለበጠ። 2 በሃይል ነከሰ፥ በጥርሱ ቦተረፈ፥ ወጋ። 3. በስለት ወጋ፥ ቀደደ፥ ዘነጠለ። 4. ዘረዘረ፥ ሸከሸከ፥ ማግን አራርቆ ጣለ። 5. ተፈላጊውንና የማይፈለገውን ሳይለይ በሙሉ አሳለፈ፥ አወረደ (ወንፊት)። 6. (ዘይ.) የሚያውቀውን ሁሉ አወራ፥ ምስጢር አወጣ።

ዘክዛካ(ዝክዝክ) ቅ 1. ዘርዛራ፥ ሽክሽክ፡ ያልተጠቀጠቀ (ልብስ፡ ወንፊት፣...)። 2. (ዘይ.) ምስጢር የማይጠብቅ፥ ወሬኛ።

ዘካ ስ በእስልምና ሃይማኖት ከማንኛውም የስራ ውጤት ከአስር አንድ የሚሰበሰብ አስራት፣ የአስራት ክፍያ፣ ምፅዋት።

ዘኬ ስ 1. ለተዝካር ተብሎ የሚዘጋጅ እንጀራ፥...። 2. ለሙታን መታሰቢያ ተብሎ የሚዘጋጅ መክፈልት፣ ምግብና መጠጥ።

ዘክዛካ "**ዘከዘከ**" ስር ተመ.

ዘወረ ግ አዞረ፥ ጠመዘዘ፡ አሽከረከረ።

መዘወሪያ ስ ማዞሪያ፡ መጠምዘዣ፥ እጀታ።

መዘውር ስ 1. ማሽከርከሪያ፡ ማዞሪያ፡ እጀታ። 2. አንድን ነገር እንዲዞር፥ እንዲሽከረከር የሚያደርግ መካኒካዊ ጉልበት፡ ሃይል። 3. ጠፍር፡ ቋድ (የበቅሎ፥ የፈረስ መሰንከያ)። 4. የመኪና መሪ።

ዝውውር "**ዞረ**" ስር ተመ.

ዘወርዋራ "**ዞረ**" ስር ተመ.

***ዘወተረ**

ዘወትር ተው.ግ. ሁል ጊዜ፥ በየእለቱ፥ በየቀኑ።

የዘወትር የሁል ጊዜ። *የዘወትር ልብስ/ የዘወትር ጠባይ።*

ተዘወተረ ግ ተደጋገመ፥ የሁልጊዜ ድርጊት ሆነ።

አዘወተረ ግ መላለሰ፥ ደጋገመ፥ ሁልጊዜ አደረገ።

አዘውታሪ ቅ አንድን አይነት ድርጊት መላልሶ በየጊዜው የሚፈፅም።

ዘው

ዘው አለ ግ ጥልቅ፥ ግብት አለ።

ዘው ዘው አለ ግ እዚህም እዚያም ገባ፥ ጥልቅ አለ።

ዘው አደረገ ግ ጥልቅ አደረገ።

ዘውድ ስ ከወርቅ፡ ከእንቁ፥... የሚሰራና ነገስታት እንደአክሊል፥ እንደቆብ በራሳቸው ላይ የሚደፉት የንጉሲነት ማእረግ ምልክት።

ዘውድ ደፋ ነገሰ።

ዘውድ ጫነ ዝ.ከ.

የዘውድ ስርአት ስ በንጉስ የሚመራ ስረአት።

የዘውድ አማካሪ ስ የንጉስ አማካሪ።

ዘውድ

የዘውድ አገዛዝ ስ በንጉስ የሚመራ ስርአት።

***ዘየመ**

ዜማ ስ ቃና፥ ስልትና ተከታታይነት ያለው፡ የተለያዩ የሃዘን ወይም የደስታ ስሜቶችን መግለፅ የሚያስችል ሙዚቃዊ ድምፅ።

ዜማ ሰበረ ዜማው ከስንኙ ወይም ከግጥሙ ምጣኔ ጋር አልጣጣም አለ፥ ተበላሸ።

የዜማ ምልክት ስ እንደ ጭረት፡ ድፋት፥ ደረት (` ⌒ ◡) ያሉ፥ አንድ ዜማ በምን አይነትና እንዴት እንደሚዜም የሚመራ፥ የድምፅ አወጣጥን ሁኔታ የሚያሳይ ምልክት።

የዜማ ቤት ስ (ቤ.ክህ.) መንፈሳዊ የዜማ ትምህርት የሚሰጥበት ትምህርት ቤት።

አዜመ ግ 1. ዜማን አሰማ። 2. ዘፈነ፡ አንጎራጎረ።

ዘየረ ግ (እስል.) 1. ሰላም አለ፥ ሰላምታ ሰጠ። 2. በዜማ አወደሰ፥ ምስጋና አቀረበ። 3. ጎበኘ፥ ተሳለመ (ቅዱስ የሆኑ ቦታዎችን)።

ዝየራ ስ (እስል.) 1. የእጅ ሰላምታ። 2. በዜማ የሚቀርብ ውዳሴ፥ ምስጋና። 3. ጉብኝት (ቅዱስ የሆኑ ቦታዎችን)።

ዘየነ ግ አስጌጠ፥ አስዋበ፥ ሸለመ፡ አሽቀረቀረ፥ አሳመረ።

ዝይን ቅ ሽቅርቅር፡ የተዋበ፥ ያማረ።

ተዘየነ ግ አጌጠ፥ አማረ፥ ተሽቀረቀረ፡ ተዋበ።

ዘየደ ግ ብልሃት ፈጠረ፥ አበጀ።

ዘዴ ስ 1. ብልሃት፡ ጥበብ፥ እውቀት። 2. የአሰራር መንገድ፥ ስልት።

በዘዴ ተው.ግ በብልሃት።

ዘዴኛ ቅ ብልሃተኛ፥ ጥበበኛ፥ ዘዴ አዋቂ።

ዘዬ ስ 1. ፈሊጥ፥ የአሰራር መንገድ። 2. ልማድ። 3. አካባቢያዊ አነጋገር፣ ቀበልኛ።

ዘይቤ ስ 1. ውስጠ ምስጢር ያለው አነጋገር። 2. በምሳሌ፥ በንፅፅር፡... እማካይነት ንግግርን በማስዋብ ስሜትን ለመግለፅ የሚያስችል የአነጋገር ስልት።

በዘይቤ ተናገረ በቅኔ፥ ሰወር አድርጎ ተናገረ።

ዘይቤአዊ አነጋገር ስ በምሳሌ፥ በንፅፅር፥ በሰውኛ፥... አማካይነት ጎልቶ ወይም ተውቦ የሚቀርብ አነጋገር። (ለምሳሌ አንበሳ የሆነ ወንድም አለኝ / እንደ ርግብ የዋህ ሁን)።

ዘይቱን ስ ሲበስል የቆዳው ቀለም ቢጫ፥ ውስጡ ደግሞ ቀይ ወይም ነጭ የሚሆንና በትናንሽ ጠንካራ ፍሬዎች የተሞላ፥ ቆዳው ጭምር የሚበላ ሉሚ የሚያክል ፍሬ የሚያፈራ ተክል፤ ፍሬውም ዘይቱን ይባላል።

ዘይት ስ 1. እንደ ኑግ፣ ሰሊጥ፣... ካሉ የቅባት እህሎች ወይም እንደ ጉሎ ካሉ ፍሬዎች ተጨምቆ የሚወጣ ወይም ከሌሎች ነገሮች የሚዘጋጅ ቅባትነት ያለውና ከውሃ ጋር ሊቀላቀል የማይችል፣ ለምግብ ማጣፈጫነት፣ ለቅባትነት የሚያገለግል ፈሳሽ። 2. ከከርሰ ምድር ወጥቶ የሚዘጋጅና በልዩ ልዩ ሜካኒካዊ መሳሪያዎች ውስጥ (ለምሳሌ የመኪና ሞተር፣...) ፍትጊያ እንዳይኖር ለመከላከል፤ ለማለስለስ፤... የሚያገለግል፣ ከውሃ ጋር ለመቀላቀል የማይችል፣ ዝልግልግነት ያለው ፈሳሽ።

ዘይት ቀለም ስ ዘይትነት ያለው፤ ስእሎችን ወይም ልዩ ልዩ የቀለም ቅቦችን ለመስራት የሚያገለግል ቀለም።

ዘዴ **"ዘየደ"** ስር ተመ.

ዘዴኛ ዝ.ከ.

***ዘገመ**

ዘገምታ ስ ዝግታ።

ዘገምተኛ ቅ ዝግተኛ፤ ቀስ የሚል።

አዘገመ ግ በቀስታ፤ በዝግታ ተራመደ፣ ተንቀሳቀሰ።

አዝጋሚ ቅ በቀስታ የሚራመድ፤ የሚሄድ።

አዝጋሚ ለውጥ ስ በቀላሉ ግልፅ ሆኖ የማይታይ፤ ነገር ግን ቀስ በቀስ የሚካሄድ የመጠን ለውጥ።

ዘገር ስ ጦር።

ዘገበ ግ 1. አጠናቀረ፣ አዘጋጀ (ወሬን፤ ሪፖርትን፣...)። 2. ፃፈ፤ መዘገበ። 3. ሰበሰበ፣ አከማቸ፣ አጠራቀመ።

ዘገባ ስ 1. ስለ አንድ ነገር የተሰጠ ዝርዝር መግለጫ። 2. የዜና ጥንቅር።

ዘጋቢ ስ ዜና አዘጋጅ፣ አጠናቃሪ።

ዘገነ ግ በእጅ አፈሰ፤ አነሳ፣ ያዘ (እንደ ጥራጥሬ፤... ያሉትን)።

ዝግን ስ 1. ተቀቅሉ ከተመተረ በኋላ ለብቻው ከተሰራ ሽሮ ወጥ ጋር ወይም ብቻውን ሊበላ የሚችል ስጋ። 2. የስጋ ጥብስ ወጥ። 3. ዝግኝ።

ዝግኝ (ዝግን) ቅ በአንድ እጅ ብቻ የታፈሰ፣ የተዘገነ (የጥራጥሬ ወይም የሌላ ነገር መጠን)።

ተዘገነ ግ በዝግን ተነሳ፤ ታፈሰ፣ ተወሰደ (ጥራጥሬ፤ ሙሻ፣...)።

ዘገነነ ግ ሰቀጠጠ ወይም የሚያስፈራ፣ የሚያስደነግጥ ስሜት ፈጠረ።

ዘግናኝ ቅ ሰቅጣጭ፤ አስደንጋጭ፣ አሳዛኝ፣ *የመኪናው አደጋ እጅግ ዘግናኝ ነበር።*

ዘገየ ግ ቆየ፤ ወደኋላ ቀረ፤ ቀስ አለ።

አዘገየ ግ አቆየ፣ ወደ ኋላ አስቀረ።

***ዘጋጀ**

ዝግጁ ቅ የተዘጋጀ፤ ስንዱ።

ዝግጅት ስ 1. መሰናዶ። 2. የተጠናቀቀ ወይም የሚጠናቀቅ የስራ ክንውን። 3. አንድን ፅሁፍ፤ ፊልም፣ ትያትር፣... ለተደራስያን በሚቀርብ መልክ የማዘጋጀት ተግባር።

ተዘጋጀ ግ 1. ተሰናዳ። 2. ተከናወነ፤ ተቀናበረ። 3. ተሰርቶ አለቀ፤ ቀረበ።

ተዘገጃጀ ግ ተሰናዳ።

አዘጋጀ ግ 1. አሰናዳ። 2. አከናወነ። 3. ሰርቶ፤ ፅፎ አወጣ፣ አቀረበ።

ማዘጋጃ ቤት ስ የከተማን አስተዳደር በተመለከተ የተለያዩ ስራዎችን የሚሰራ መስሪያ ቤት።

አዘጋጅ ስ 1. የትያትርን፤ የፊልምን ዝግጅት የሚሰራ (ሰው)። 2. መፅሄትን፤ ጋዜጣን ወይም መፅሃፍን አጠናቅሮ የሚያወጣ ግለሰብ ወይም ድርጅት። 3. አንድ አይነት ፕሮግራም፤ ሴሚናር፤ ስብሰባ፣ እንዲካሄድ የሚያደርግ፣ የሚያቀነባብር ግለሰብ ወይም ድርጅት።

ዘገጠ ግ ዘቀጠ፤ ሰረገ፤ ሰጠመ።

አዘገጠ ግ 1. አዘቀጠ፤ አሰረገ፤ አሰጠመ። 2. ዘገጠ።

ዘጊ^1 **"ዘጋ"** ስር ተመ.

ዘጊ^2 **"*ዘጋ"** ስር ተመ.

ዘጋ ግ 1. ገጠመ፣ ከደነ፤ ደፈነ (በርን፤ መፅሃፍን፣ ...)። 2. እንዲያቆም፣ እንዲያቋርጥ አደረገ። *ሬዲዮኑን ዘጋ/ቧንቧውን ዘጋ።* 3. አገደ፤ ከለከለ (መተላለፊያን፣...)። 4. ከሰው ተለይቶና ቤት ዘግቶ ሱባኤ ያዘ፤ ለብቻው ተቀመጠ (ባህታዊ)። 5. የምግብ ፍላጎት አሳጣ፤ ምግብ ከለከለ፤ አስጠላ። 6. አጠቃለለ፤ ደመደመ፣ ጨረሰ። 7. አንቆ ያዘ፣ አላናግር አለ። *ጉንፋን ድምፄን ዘጋው።* 8. (የአራዳ አነ.) ዝም አለ፤ አኮረፈ። 9.(የአራዳ አነ.) አስጠሊታ፣ አስቀያሚ ሆነ።

መዝጊያ ስ 1. የበር ግጣም፤ ሳንቃ። 2. መከደኛ። 3. ሬዲዮ፤ ቧንቧ ወይም ሌላ ነገር በማያስፈልግበት ጊዜ እንዳይሰራ ማቆሚያ። 4. መደምደሚያ፤ ማጠቃለያ (የፅሁፍ፣ የሃሳብ፣ የስብሰባ፤...)።

ዘጊ ቅ (ተራ አነ.) ደስ የማይል፣ አስቀያሚ፤ አስጠሊታ።

ዝግ ቅ 1 የተከደነ፤ የተደፈነ፣ የተቆለፈ። 2 የተከለከለ፣ የታገደ (መንገድ)። 3 ስራ ያቆመ። 4 (ዘይ.) የማይናገር፣ ሁሉንም ነገር በሆዱ አምቆ የሚይዝ።

ዝግ ስብሰባ ስ ከተፈቀደላቸው የተወሰኑ ሰዎች በስተቀር ሌላ ሳይገባበት የሚካሄድ ስብሰባ።

ዝግ ችሎት ስ ለአደባባይ፤ ለህዝብ ክፍት ሳይሆን የሚመለከታቸው ሰዎች ብቻ ባሉበት የሚካሄድ ችሎት፣ ዳኝነት።

ተዘጋ ግ 1. ተደፈነ። 2. ታገደ፣ ተከለከለ፤ የማያሳልፍ ሆነ። *መንገድ ተዘጋ።* 3. ዝም አለ። 4. ስራ አቆመ (ት/ቤት፣ ፋብሪካ፣...)።

*ዘጋ

ዘጊ ቅ የሚያደራ (ድርን)። *እንደ ዝሃ ዘጊ ምን ያመላለሰሻል።*

አዘጋ ግ ድር ወይም ዝሃ አደራ፤ ዘረጋ።

አዝጊ ቅ አድሪ፣ ድርን የሚያደራ።

ዘጋቢ **"ዘገበ"** ስር ተመ.

ዘግናኝ **"ዘገነነ"** ስር ተመ.

*ዘጎረጎረ

ዝጉርጉር (ዥጉርጉር) ቅ ጠቃጠቆ (የነጭና ጥቁር ወይም የተለያዩ ቀለማት ስብጥር)።

ተዝጎረጎረ (ተዥጎረጎረ) ግ የተለያዩ ቀለማት ስብጥር ወይም ቡራቡሬ ሆነ።

አዝጎረጎረ(አዥጎረጎረ) ግ የተለያዩ ቀለማት ስብጥር ወይም ቡራቡሬ አደረገ።

ዘጠረ ግ 1. በብዛት ጨመረ፣ ሞጀረ። 2. ገጠገጠ፣ ተከለ (ድንኳንን)። 3. ነፋ፣ ወጠረ (ሆድን)።

ዝጥር ቅ ውጥር፣ የተወጠረ።

ተዘጠረ ግ 1. በብዛት ተጨመረ፣ ተሞጀረ። 2. ተገጠገጠ፤ በብዛት ተተከለ (ድንኳን)። 3 ተነፋ፣ ተወጠረ፣ አበጠ።

ዘጠና ስ 1. በሰማንያ ዘጠኝና በዘጠና አንድ መካከል ያለ ቁጥር መጠሪያ፤ በአሃዝ ሲፃፍ፣ '90' ነው። **ቅ** 2. ብዛቱ፤ መጠኑ ዘጠኝ ጊዜ አስር ያህል የሆነ። *ዘጠና ብር።*

ዘጠኝ ስ 1. በስምንትና በአስር መካከል ያለ ቁጥር መጠሪያ፤ በአሃዝ ሲፃፍ '9' ነው። **ቅ** 2.መጠኑ ወይም ብዛቱ በስምንትና በአስር መካከል የሆነ። *ዘጠኝ መፃሃፎች።*

*ዘጠዘጠ

ዘጠዘጥ (ዘጥዛጣ) ቅ (ስድብ) አፋዳሽ፣ አውደልዳይ፤ ያለ ስራ ከወዲያ ወዲህ እያለ የሚያረጠርጥ።

ዘጥ ዘጥ(ዘጭ ዘጭ) አለ ግ 1. አዘጠዘጠ፣ አረጠረጠ። 2. ሩጫ አይሉት ርምጃ አይነት አካሄድ ሄደ (ብዙውን ጊዜ ወፍራም ሰው)።

አዘጠዘጠ ግ አውደለደለ፣ አፋደሰ።

አዘጥዛጭ ቅ ስራ የማይሰራ፣ አውደልዳይ፤ አረጥራጭ።

ዘጥ

ዘጥ አለ (ዘጭ አለ) ግ ዱብ አለ፤ ወደቀ።

ዘጥዛጣ "*ዘጠዘጠ" ስር **"ዘጠዘጥ"**ን ተመ.

ዘጭ አለ "ዘጥ" ስር ተመ.

ዘፈር ስ ዘርፍ።

ዘፈቀ ግ 1. ደፈቀ፣ ነከረ፤ አስገባ፣ አሰመጠ፤ ከተተ (ውሃ ውስጥ)። 2. (ዘይ.) ከተተ፣ አስገባ (እዳ፣ መከራ፣... ውስጥ)።

ዝፍቅ ቅ (ስድብ) ሞኝ፣ ቂል።

ተዘፈቀ ግ 1. ተነከረ፣ ገባ፣ ሰጠመ (ውሃ ውስጥ)። 2. ገባ (እዳ፣ መከራ፣... ውስጥ)።

ዘፈነ ግ 1. አዜመ፣ አንጎራጎረ (ዘፈንን)። 2. ዘፈንን፣ ዜማን አሰማ (ሬዲዮ፣ ቴፕ)። 3. ተንቀጠቀጠ፣ ተንዘፈዘፈ (ሰውነት)።

ዘፈነብኝ ተረገረገብኝ፣ የስድብና የቁጣ ንግግር ተናገረኝ።

ዘፈን ስ ዜማ፣ እንጉርጉሮ (ዓለማዊ የሆነ)።

ዘፈን አወረደ ዘፈኑን በዜማ፣ በእንጉርጉሮ መራ፤ አቀነቀነ።

ዘፈን አወጣ አዳዲስ ዘፈኖችን አቀረበ፣ ደረሰ፣ ለህዝብ አሰማ።

ዘፋኝ ቅ ድምፃዊ ተጫዋች፣ አንጎራጓሪ።

አስዘፈነ ግ ሰውን፣ ሬዲዮን ወይም ቴፕን፣ እንዲዘፍን፣ ዘፈን እንዲያሰማ አደረገ።

ዘፈዘፈ ግ 1. እንዲርስ ውሃ ውስጥ ለብዙ ሰአት አቆየ፣ ነከረ፣ ዘፈቀ (ጥራጥሬን፣ ልብስን፣ ...)። 2. ከመረ፣ ቆለለ። 3. በብዛት ቆረጠ፣ ረፈረፈ፣ ለሸለሸ (ዛፍን)።

ዘፋዘፎ ቅ ረዥምና ወፍራም፣ ሰውነተ ከባዳ የሆነ፣ ቅርፅቢስ።

ዝፍዛፋ ዝ.ከ.

ዝፍዝፍ ቅ 1. እንዲርስ የተነከረ። 2. (ስድብ) ረሀጥ፣ ከተቀመጠበት የማይነሳ፣ ሰነፍ።

ተዘፈዘፈ ግ 1. ውሃ ውስጥ ተነከረ (እንዲርስ)። 2. ስራ ሳይሰራ ተቀምጦ ዋለ፤ ተረፈተ፣ ሰነፈ።

*ዘፈዘፈ

ተንዘፈዘፈ ግ ተንቀጠቀጠ።

አንዘፈዘፈ ግ አንቀጠቀጠ።

*ዘፈጠጠ

ዘፍጣጣ (ዝፍጥጥ) ቅ ሆደ ዘርጣጣ፣ ገፍጣጣ።

ዝፍጥጥ አለ ግ ተንዘፈጠጠ።

ተንዘፈጠጠ ግ ተንዘረጠጠ፤ ተንገፈጠጠ (ሆድ፣ ...)።

አንዘፈጠጠ ግ አንዘረጠጠ፤ አንገፈጠጠ፤ (ሆድን፤ ...)።

ዘፈፈ ግ ተንዛፈፈ።

ዘፋፋ ቅ 1. ትልቅነትና ስፋት ያለው (የዛፍ ቅርንጫፍ)። 2. እርዝማኔና ክብደት ያለው (አካላዊ አቋም)። 3. ዘርፋፋ፣ ሰፊና ረጅም (ልብስ)።

ተንዛፈፈ ግ 1. ሰፋ፤ ተንሰራፋ፣ ተዘረጋ (የዛፍ ቅርንጫፍ)። 2. ተንዘረፈፈ፤ ረዘመ (ልብስ)።

ዘፋኝ "ዘፈነ" ስር ተመ.

ዘፋዘፎ "ዘፈዘፈ" ስር ተመ.

ዘፋፋ "ዘፈፈ" ስር ተመ.

ዘፍ

ዘፍ አለ ግ በቁመቱ ሙሉ ወደቀ፤ ተጋደመ።

ዘፍ አደረገ ግ በቁመቱ ሙሉ እንዲወድቅ አደረገ፤ ጣለ።

ዘፍዛፋ "ዘፈዘፈ" ስር ተመ.

ዘፍጣጣ "*ዘፈጠጠ" ስር ተመ.

ዙ የ"ዘ" ፊደል ካእብ ዘር።

ዙሬት "ዞረ" ስር ተመ.

ዙሪያ ዝ.ከ.

ዙር ዝ.ከ.

ዙርያ "ዞረ" ስር "ዙሪያ"ን ተመ.

ዙሮሽ ዝ.ከ.

ዙማ ቅ ወፈር ያለ፣ አጭር (ሰው)።

ዙጥ

ዙጥ አደረገ ግ ፈሳ።

ዙፋን ስ 1. የንጉስ መንበር፤ አልጋ። 2. ንጉሰ የሚቀመጥበት የተጌጠ ትልቅ ወንበር።

ዙፋን ቤት ስ የንጉሰ ዙፋን የሚቀመጥበት ቤት።

ዙፋን ችሎት ስ ንጉስ በዳኝነት የሚቀመጥበት ችሎት።

ዚ የ"ዘ" ፊደል ሳልስ ዘር።

ዚቅ ስ 1. (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) በማህሌት ጊዜ ከመልክ መረግድ ቀጥሎ በፀናፅልና በከበሮ እየታጀበ የሚባል ዜማ። 2. የዜማ መፅሃፍ ስም።

ዚቅ አወረደ በከበሮና በፀናፅል እየታጀበ አዜመ (ዚቅን)።

ዚቀኛ ቅ ተረበኛ፣ ተረብ አዋቂ።

ዚፕ ስ በዘሁን ጊዜ እንደሱሪ፣ ጃኬት ያሉ ልብሶችን ለመቆለፍ ወይም እንደሻንጣ፤ ቦርሳ የመሳሰሉትን ለመዝጋት የሚያገለግል ተወሳሳቢ ወይም እርስ በርሱ የሚሰካካ ጥርስ ያለው መቆለፊያ፤ ቻርኔላም ይባላል።

ዛ የ"ዘ" ፊደል ራብእ ዘር።

ዛሀርት ስ ትልቅ ሆድ።

ዛሀርታም ቅ ሆዳም።

ዛለ ግ ደከመ፤ አቅም አጣ፣ ተልፈሰፈሰ።

ዝለት ስ ድካም፣ አቅም ማጣት።

አዛለ ግ አደከመ፣ አቅም አሳጣ፤ አልፈሰፈሰ።

ዛላ ስ 1.ፍሬ ያዘለ የሰንደ፣ የገብስ፣ ... ራስ፤ እልፍ። 2.የሰውነት አቋም፤ ቁመና።

ዛላ በርበሬ ስ የበሰለ ወይም የቀላ ቃሪያ።

ዛራም "ዛር" ስር ተመ.

ዛሬ ስ 1. በትናንትናና በነገ መሃል ያለ ጊዜ፣ ያለንበት ቀን። 2. የአሁኑ ዘመን። *በዛሬው ጊዜ እህል ተወደደ።*

ዛሬ ነገ አለ አመነታ፤ ቀጠሮ አበዛ፣ በተፈለገው ጊዜ፣ ቀን፤... ሳያደርግ፣ ሳይፈፅም ቀረ (ጉዳዩን፣...)።

ዛር ስ ውቃቢ፣ የሚያስጓራ ክፉ መንፈስ።

ዛር አንጋሽ ቅ ጠንቋይ፤ ቃልቻ፤ የዛር ባለሟል፣ ዛር እነጋጋሪ ነኝ የሚል።

የዛር ውላጅ ስ ዛር የወለደው፣ ስጋ የለበሰ ጋኔን ነው ተብሎ የሚታመን (ርኩስ መንፈስ)።

የዛር ፈረስ ቅ ዛር የያዘው (ሰው)።

ዛራም ቅ 1. ዛር ያለበት። 2. ክልፍልፍ፣ ቀዥቃዣ። 3. ቁጡ፣ ነጭናጫ።

ዛቀ ግ 1. አፈሰ፣ በብዛት ወሰደ። 2. ጧጠጠ፣ ሟጠጠ፣ ጠረገ። 3. ደነቆለ፣ ጠነቆለ (አይንን)።

መዛቂያ ስ እንደ አካፋ፣ ማንኪያ ያለ ማፈሻ፣ ማንሻ እቃ።

ዝቆሽ ነው በትንሽ ዋጋ የተገዛው ነገር በጣም ብዙ ነው።

ተዛቀ ግ 1.ታፈሰ፣ በብዛት ተወሰደ። 2. ተሟጠጠ፣ ተጠረገ። 3. በርካሽ ተገኘ።

ዛቀጠ ግ ሰፋ፣ ማሰነ።

ዛቆነ^1 ግ ዲያቆን ሆነ፣ ዲቆነ።

አዛቆነ ግ ዲያቆን አደረገ፤ አዲቆነ።

ዛቆነ^2 ግ ሰፋ፣ ደከመ።

አዛቆነ ግ አሰፋ፣ አደከመ።

ዛበረ ግ 1. ሰፋ፤ ባከነ። 2. ቃዠ፣ ለፈለፈ።

ዛባሪ ቅ ለፍላፊ፣ ቀላማጅ።

አዛበረ ግ 1. አሰፋ፣ አደከመ። 2. አቃዠ፣

አስለፈለፈ።

ዛቢያ ስ 1. የመጥረቢያ፣ የዶማ፣... እጀታ። 2. መሬትን መሃል ለመሃል ሰንጥቆ የሚያልፍና መሬት የምትሽከረከርበት የሃሳብ መስመር።

ዛቢያ ግንጥል ጉልበታም፣ ፈርጣማ ጡንቻ ያለው (ሰው)።

ዛባሬ "**ዛበረ**" ስር ተመ.

ዛብ ስ የበቅሎ ወይም የፈረስ ልጓም ቋድ፣ ጠፍር።

ዛተ ግ አስፈራራ፣ ጉዳት እንደሚያደርስ ተናገረ፣ ፎከረ።

ዛቻ ስ የማስፈራራት ንግግር፣ ፉከራ።

ዛቲ ስ በቤተክርስቲያን ለሰዎች የሚታደል ከየቤቱ የመጣ የዳቦ፣ የአንባበር፣ የእንጀራ ቁራሽ፣...፣ ጣዲቅ።

ዛቻ "**ዛተ**" ስር ተመ.

ዛኒጋባ ስ ጣሪያው ባለ አንድ አቅጣጫ ወይም ተፋሰስ የሆነ አነስተኛ ቤት።

ዛንታ ስ ወግ፣ ታሪክ።

ዛዛቴያም "***ዛዛ**" ስር ተመ.

ዛዛቴ ዝ.ከ.

ዛዘለ ግ ረዘመ፣ ተንተተ፣ተንገርለገለ።

ዛዘን ግ 1 ዞረ፣ ባዘነ፣ናበዘ። 2 ሾፈደ፣ ፈለገ(ዝሙት)።

ዛዛኝ ቅ ሻፋዳ።

*ዛዛ

ዛዛቴ ስ የተንዛዛ፣ ከልክ ያለፈ ወሬ፣ ነገር።

ዛዛቴያም ቅ ነገር ቶሎ የማይቆርጥ፣ ወሬኛ።

ተንዛዛ ግ ከመጠን አለፈ ፣ በጣም በዛ።

አንዛዛ ግ ከመጠን አሳለፈ፣በጣም አበዛ።

ዛዛኝ "**ዛዘን**" ስር ተመ.

ዛገ ግ አፈር ላይ በመውደቁ ወይም እርጥበት በማግኘቱ፣ ሳይሰራበት በመቆየቱ፣... መልኩ ተቀየረ፣ ተበላሸ፣ አፈር መሰለ(ብረት)።

ዝገት ስ አፈር ላይ ከመውደቅ፣ እርጥበት ላይ ከመቆየት፣... የተነሳ ብረታ ብረት በሆኑ ነገሮች ላይ የሚደርስ አፈር የመምሰልና የመበላሸት ሁኔታ።

አዛገ ግ አበላሸ፣ ዝገት እንዲይዝ አደረገ(ብረታ ብረትን)።

ዛጎለ ግ ዛጎል መሰለ፣ እንደመንጣት አለ።

ዛጎል ስ በባህር ውስጥ የሚኖሩ አንዳንድ ነፍሳት በህይወት እያሉ ለሰውነታቸው ጠንካራ ልባስ ሆኗቸው የሚኖርና ከሞቱ በኋላ እንደ ጌጥ የሚያገለግል ጠጣር አካል።

ዛጎል ጣለ ዛጎል መሬት ላይ በመጣል ጠንቆለ።

ዛጎል ጣይ ስ ዛጎል በመበተን የሚጠነቁል ጠንቋይ፣ ሟርተኛ።

ዛጎል በርበሬ ስ ቀይ ጣሳ በርበሬ፣ በቀይ ቀለሙ ላይ ነጭ የጣለበትና ጥራቱ ዝቅተኛ የሆነ በርበሬ።

ዛጎልማ ቅ መልኩ፣ ቀለሙ ዛጎል የሚመስል።

ዛፍ ስ 1. ግንድና ቅርንጫፎች ያሉት፣ መጠኑ ትልቅና ትንሽ የሆነ፣ ለረጅም ጊዜ ሊቆይ የሚችል የእፅዋት አይነት። 2. (ዘይ.) ረጅም (ሰው)።

ዛፍ 1ኛ ፍቺ

ዛፍ ቆራጭ ስ ስራው ዛፍ መቁረጥና መፍለጥ የሆነ ሙያተኛ ።

ዜ የ "**ዘ**" ፊደል ሃምስ ዘር ።

ዜማ "***ዘየመ**" ስር ተመ.

ዜሮ ስ ባዶ፣ ምንም፣ በአሃዝ ሲፃፍ "0" ነው። *ተወዳዳሪዎቹ ያለ ውጤት ዜሮ ለዜሮ ተለያዩ።*

ዜሮ ሻማ ስ እጅግ በጣም አነስተኛ የሆነ ብርሃን ያለው የከረንቲ አምፑል።

ዜና ስ ወሬ።

ዜና መዋእል ስ የቀድሞ ነገስታት የእለት ወይም የጦርነት ውሎአቸው ተመዝግቦ የሚገኝበት መፅሃፍ።

ዜና ማሰራጫ ስ እንደሬዲዮ፣ ቴሌቪዥን፣ ጋዜጣ ያሉ ዜና ማስተላለፊያ።

ዜና እረፍት ስ የአንድ ሰው የመሞቱ ወሬ።

ዜጋ ስ በአንድ ሃገር ውስጥ በመወለዱ ወይም ፈቃድ በማግኘቱ የተወላጅነት መብት ያለው ሰው።

ዜግነት ስ በአንድ አገር ውስጥ በተወላጅነት ወይም በፈቃድ የሚገኝና ሰውዬው የዚያ አገር ሰው የመሆኑ መገለጫ።

ዝ የ "**ዘ**" ፊደል ሳድስ ዘር።

ዝሃ(ዘሃ) ስ ድር።

ዝሃ አዘጋ ድር አደራ።

ዝሃ በዝሃ ድር በድር፣ ማጉም ድር የሆነ (ልብስ)።

ዝሆኔ ስ እግር የሚያሳብጥ በሽታ፤ ኮብሸ።

ዝሆን (ዘሆን) ስ በጣም ትላልቅ የሆኑና ከከንፈሩ ወደ ውጪ የወጡ ሁለት ጥርሶች፣ ሰፋፊ ጆሮዎችና አንድ ኩምቢ ያለው፣ ምግቡ በአብዛኛው ሳርና ቅጠላቅጠል የሆነ ግዙፍ እንስሳ (ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።።

የዝሆን ጥርስ ስ በላይ በኩል ከከንፈሩ ውጪ የሚታይና 5 ሜትር ያህል ርዝማኔ ያለው፤ ብዙውን ጊዜ በጌጥነት የሚያገለግል፤ ነጭ ሆኖ ወፍራምና ረጅም ቀንድ የሚመስል የዝሆን የውሻ ክራንቻ።

ዝለቅ "ዘለቀ" ስር ተመ.

ዝለት "ዛለ" ስር ተመ.

ዝላይ "ዘለለ¹" ስር ተመ.

ዝልል "ዘለለ²" ስር ተመ.

ዝልንግድ ቅ 1. ረዥም፤ ቀውላላ። 2. የማይረባ፤ ሰነፍ ።

ዝልዝል "ዘለዘለ" ስር ተመ.

ዝልጉስ "ዘለጎሰ" ስር ተመ.

ዝልጊት ስ የጠላ፤ የጠጅ ማጥለያ ወንፊት፤ ወንጠፍት።

ዝልግልግ "*ዘለገለገ" ስር ተመ.

ዝልፊያ "ዘለፈ¹" ስር ተመ.

ዝልፍልፍ "*ዘለፈለፈ" ስር ተመ.

ዝሙተኛ "ዘሞተ" ስር ተመ.

ዝሙት ዝ.ከ.

ዝማሜ "ዘመመ¹" ስር ተመ.

ዝማም¹ ስ እንዳይበሳ ወይም እንዳይጠጣ በከብት አፍ ላይ የሚጠለቅ ቅርጫት መሰል መሸበቢያ፤ ልጓም።

ዝማም² ቅ ያማረ፤ የተዋበ፤ የተወለወለ።

ዝማም ወርቅ ስ 1. በተደጋጋሚ የተነጠረ ወርቅ። 2. በጆሮ ወይም በአፍንጫ ላይ የሚንጠለጠል ወርቅ።

ዝማሬ "ዘመረ" ስር ተመ.

ዝም

_ብሎ ዝም ነው ተሩ፤ የሚያነቅ፤... ነው። *መሃያፍ ብሎ ዝም ነው።*

ዝምታ ስ 1. አለመናገር። 2. ፀጥታ።

ዝምተኛ ቅ ብዙ የማይናገር፤ ጭምት።

ዝም አለ ግ 1. ሳይናገር ቀረ፤ ጭጭ አለ። 2. መልስ ሳይሰጥ ቀረ። 3. ምንም አይነት ርምጃ፤ እንቅስቃሴ ሳያደርግ ቀረ፤ ተወ።

ዝም ብሎ 1. ያለምክንያት። *ዝም ብሎ ቀጣው*። 2 ባለማቋረጥ። *ዝም ብሎ ይፈላል*። 3. ምንም ሳይናገር፤ ሳያደርግ፤...። *ዝም ብሎ ሄደ።*

ዝም አሰኘ ግ ዝም እንዲል፤ እንዳይናገር፤ ድምፅ እንዳያሰማ አደረገ፤ ፀጥ አደረገ።

ዝምባም "ዝንብ" ስር ተመ.

ዝምብ ዝ.ከ.

ዝምተኛ "ዝም" ስር ተመ.

ዝምታ ዝ.ከ.

ዝምዝማት "ዘመዘመ" ስር ተመ.

ዝምዝም "ዘመዘመ" ስር "ዝምዝማት"ን ተመ.

ዝምድና "*ዘመደ" ስር ተመ.

ዝራት "ዘራ" ስር ተመ.

ዝራንጭ ስ የቀንጮ አይነት።

ዝር "ዘራ" ስር ተመ.

ዝርክራኪ "*ዘረከረከ" ስር ተመ.

ዝርክርክ ዝ.ከ.

ዝርዝር "ዘረዘረ" ስር ተመ.

ዝርያ "ዘራ" ስር ተመ.

ዝርግ "ዘረጋ" ስር ተመ.

ዝርግፍ "ዘረገፈ" ስር ተመ.

ዝርጥርጥ "*ዘረጠ" ስር "ዘረጥራጣ"ን ተመ.

ዝርጥጥ "ዘረጠጠ" ስር ተመ.

ዝርፊያ "ዘረፈ¹" ስር ተመ.

ዝርፍጥ "*ዘረፈጠ" ስር ተመ.

ዝቃቅቤ "ዘቃቅቤ" ን ተመ.

ዝቃጫም "ዘቀጠ" ስር ተመ.

ዝቃጭ ዝ.ከ.

ዝቅ

ዝቅታ ስ ታችኛ ቦታ፤ የከፍታ ተቃራኒ።

ዝቅተኛ ቅ 1. አነስተኛ። *ዝቅተኛ ደመወዝ ያገኛሉ*። 2. ጎድጓዳ፤ ረባዳ፤ ዘበጣ (ቦታ)። 3. የበታች።

ዝቅ አለ ግ 1. ወደ ታች ወረደ። 2. አነሰ።

ዝቅ አደረገ ግ 1. ወደ ታች አወረደ። 2. አሳነሰ ።3. ከደረጃ፤ ከማእረግ አወረደ።

ዝቅ አድርጎ ተመለከተ በማኮሰስ፤ በንቀት ተመለከተ ።

ዝቅዝቅ "ዘቀዘቀ" ስር ተመ.

ዝቅጥቃጭ "ዘቀጠ" ስር ተመ.

ዝቡጥቡጥ "*ዘበጠበጠ" ስር ተመ.

ዝባዝንኬ ስ 1. ዝግንትል፤ ኮተት። ቅ 2. የማይረባ (ለነገር)።

ዝባዝንኪ.ያም ቅ ዝግንትላም፣ ኩተታም ።

ዝባድ ስ ጥርኝ ከሚባል አውሬ የሚገኝና ሽቶ ለመስራት የሚያገለግል እንደ ጆሮ ኩክ ያለ የወዝ ወይም የላበት ግግር።

ዝብርቅርቅ "ዘባረቀ" ስር ተመ.

ዝብብት "ዘበተ" ስር ተመ.

ዝብድይ ስ እግራም ጣባ፣ ወጭት።

ዝተት ስ 1. ከበግ ፀጉር የሚሰራ (እንደባና፣ ማቅ፣...ያለ) የብርድ ልብስ አይነት። ቅ 2. (ስድብ) የማይረባ፣ ቅልጥፍና የሌለው። 3. የተቀዳደደ፣ የተጣጣፈ አሮጌ ልብስ፣ ቡትቶ።

ዝተታም ቅ (ስድብ) ዝተት ወይም አሮጌና የተቀደደ ልብስ የሚለብስ፣ ቅርንጥሳም።

ዝነኛ "ዝና" ስር ተመ.

ዝና ስ 1. ታዋቂነት። 2. ታሪክ። *ትልቅ ዝና ያለው ሰው ነው።* 3. ወሬ። *በዝና አውቀዋለሁ* ።

ዝነኛ ቅ ታዋቂ፣ ስመጥር ።

ዝናር ስ ዙሪያውን የጥይት መያዣዎች ያሉት፣ ብዙውን ጊዜ ወታደሮች ወገባቸው ላይ የሚታጠቁት ሰፊ ቀበቶ።

ዝናም "ዘነበ" ስር "ዝናብ"ን ተመ.

ዝናባማ "ዘነበ" ስር ተመ.

ዝናብ ዝ.ክ.

ዝንቅ "ዘነቀ" ስር ተመ.

ዝንባሌ "ዘነበለ" ስር ተመ.

ዝንባም "ዝንብ" ስር ተመ.

ዝንብ

ዝንብ(ዝምብ) ስ ከንብ አነስ የምትልና ቆሻሻ ባለበት አካባቢ የምትገኝ በራሪ ነፍሳት።

ዝንብ በል ስ መጠኑ የመስቀል ወፍ የሚያህል፣ ጭራው ረጅም፣ ጭንቅላቱ ጥቁር ሰማያዊ የሆነና ቁንጮ ያለው፣ በወንዝ አካባቢ የሚኖርና ነፍሳትን የሚመገብ ወፍ።

ዝንብ ከልክል ስ ሊማት፣ የመሶብ አይነት።

ዝንባም(ዝምባም) ቅ 1. (ስድብ) ንፅህና የሌለው፣ ቆሻሻ። 2. ፈዛዛ፣ ገልጃጃ።

ዝንተ ዓለም ተው.ግ. ዘለአለም፣ ሁልጊዜ።

ዝንኪሳ ስ ፍሬው ለማቅለሚያነት የሚያገለግል ደም የሚመስል ቀለም ያለው እሾሃማ የእፀዋት አይነት ።

ዝንዘና "ዘነዘነ" ስር ተመ.

ዝንጀሮ(ጆንጀሮ) ስ 1. ከትከሻው ከፍ ከወደ ዳሌው አጠር የሚል፣ በአንገቱና በትከሻው አካባቢ ያለው ፀጉር ጎፈርማ የሆነ፣ ፊቱና መቀመጫው ላይ ፀጉር የሌለው፣ በቆላም በደጋም መኖር የሚችል የዱር አውሬ (ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)። 2. (ስድብ፣ ዘይ.) መልከ ጥፉ።

ዝንጅብል(ጅንጅብል) ስ እንደ ድንች በመሬት ውስጥ የሚንሰራፋ፣ ስሩ በቅመምነት የሚያገለግል ተክል፣ ከስሩ የሚገኘውና በቅመምነት የሚያገለግለው ክፍልም ዝንጅብል ይባላል።

ዝንጉ "ዘነጋ" ስር ተመ.

ዝጉርጉር "*ዘጎረጎረ" ስር ተመ.

ዝንጋታ "ዘነጋ" ስር ተመ.

ዝንጣይ "ዘነጠለ" ስር ተመ.

ዝንጣፊ "ዘነጠፈ" ስር ተመ.

ዝንጥል "ዘነጠለ" ስር ተመ.

ዝክር "ዘከረ" ስር ተመ.

ዝክዝክ "ዘከዘከ" ስር ተመ.

ዝውውር "ዘወረ" ስር ተመ.

ዝየራ "ዘየረ" ስር ተመ.

ዝይ ስ ዳክዬ የሚመስል፣ ዝንጉርጉር ግራጫ ቀለም ያለው፣ አፉ ከዳክዬ አፍ ጠበብ የሚል፣ በወንዝና በባህር አካባቢ የሚኖር የአሞራ አይነት(ስእሉን አሞራ ስር ተመ.)።

ዝይን "ዘየነ" ስር ተመ.

ዝገት "ዛገ" ስር ተመ.

ዝግ

ዝግታ ስ ቀስታ፣ ፍጥነት የሌለው ሁኔታ።

ዝግተኛ ቅ ቀስተኛ፣ የማይቸኩል፣ ረጋ ያለ።

ዝግ አለ ግ ቀስ አለ፣ ፍጥነት ቀነሰ ።

ዝግ አደረገ ግ ቀስ አደረገ፣ ፍጥነቱን ቀነሰ ።

ዝግ "ዘጋ" ስር ተመ.

ዝግባ ስ በደጋ ወይም በወይና ደጋ የሚበቅል፣ ሁልጊዜ ልምላሜ የማይለየው፣ በጣም ወፍራም የሆነና ቀጥ ብሎ የሚወጣ ረጅም ግንድ ያለው ዛፍ።

ዝግባ ያህላል በጣም ግዙፍ ነው (ለሰው)።

ዝግታ "ዝግ" ስር ተመ.

ዝግን "ዘገነ" ስር ተመ.

ዝግንትል ስ የማይረባ፣ ኩተት።

ዝግንትላም ቅ ኩተታም።

ዝግኝ "ዘገነ" ስር ተመ.

ዝግጁ "*ዘገጀ" ስር ተመ.

ዝግጅት ዝ.ክ.

ዝጥር "ዘጠረ" ስር ተመ.

ዝፍቅ "ዘፈቀ" ስር ተመ.

ዝፍት^{1} ስ ከእንጨት የሚገኝ ቅጥራን፣ መጣበቅ የሚሆን ሙጫ ::

ዝፍት^{2} ስ 1. አተላ፤ ዝቃጭ:: ቅ 2. (ዘይ.) ሰነፍ::

ዝፍዝፍ "ዘፈዘፈ" ስር ተመ.

ዝፍጥጥ "*ዘፈጠጠ" ስር "ዘፍጣጣ"ን ተመ.

ዞ የ"ዘ" ፊደል ሳብእ ዘር::

ዞላ ስ ስራ መፍታት፣ ቦዘን::

ዞላ ዋለ ግ ቦዘነ፤ ስራ ፈታ::

ዞማ ቅ ለስላሳ፤ ያማረ (ፀጉር)::

ዞረ ግ 1. በአንድ ነገር ዙሪያ ሄደ፤ ከበበ:: *ታቦቱ ቤተክርስቲያኑን ለሰባት ጊዜ ዞረ*:: 2. ተሽከረከረ፤ ክብ ሰራ፤ ሾረ:: 3. የነበረበትን ቦታ፣ አቅጣጫ ቀየረ፤ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ተሳለፈ:: 4. ብዙ ቦታ ሄደ፤ ደረሰ:: *አለምን ዞረ*:: 5. ወዲያና ወዲህ ሄደ፤ ተንቀዋለለ:: 6. ወደ ሌላ ተላለፈ፤ ተሸጋገረ::

ዞረሽ እቀፊኝ(አዙረሽ እቀፊኝ) ስ በተሞቀ አሬራ (ወገሚት) ላይ ወተት ተጨምሮ የሚዘጋጅ የአይብ አይነት ::

ዞረበት 1. ግራ ተጋባ፤ ተምታታበት:: 2. አተከረበት፤ አጥብቆ ያዘው፤ ጠመደው::

መዞሪያ ስ መታጠፊያ::

ዘዋራ ቅ 1. ሰዋራ (ቦታ):: 2. ጠመዝማዛ (መንገድ)::

ዙሪያ(ዙርያ) ቅ 1. ክብ:: ስ 2. አካባቢ:: 3. ዳር፤ የአንድ አካል ጠርዝ::

ዙሪያ ነው ጠመዝማዛ ነው (መንገድ፤ ነገር)::

ዙሪያ ገባው አካባቢው በሞላ::

ዙሪያ ጋሜ ስ መሃሉ ተላጭቶ በራስ ዙሪያ የሚቀር ፀጉር (ስእሉን ፀጉር አሰራር ስር ተመ.)::::

ዙሪያ ጥምጥም ቅ ቀጥተኛነት የሌለው፤ ጠመዝማዛ የሆነ ረዥም (መንገድ)::

ዙር ቅ 1 ክብ:: ስ 2 አንድ የደርሶ መልስ ጉዞ:: 3 አንድ የተወሰነ ድርጊት የሚከናወንበት ጊዜ:: *1ኛ ዙር/ 2ኛ ዙር*:: 4. ተራ::

ዙረት ስ 1. የተወሰነ አላማ ሳይኖር ከቦታ ወደ ቦታ መሄድ፤ መንሸራሸር:: 2. ኡደት፤ በአንድ አካል ዙርያ የመሄድ፤ የመንቀሳቀስ ድርጊት::

ዟሪ ቅ 1. ከአንድ ቦታ ወደ አንድ ቦታ ወይም ወደተለያየ ቦታ የሚሄድ፤ አንድ ቦታ ረግቶ የማይቀመጥ:: 2. የተላለፈ፤ የሚተላለፍ (ከአንድ ገፅ ወደሌላው) ::

ዞር አለ ግ 1. ገለል አለ:: 2. ጠምዘዝ አለ ::

ዞር አለበት 1. አመመው:: 2. ግራ ተጋባ፤ ተምታታበት::

ዞር አደረገ ግ 1. ገለል አደረገ:: 2. አሸሸ:: 3. ጠምዘዝ አደረገ፤ አቅጣጫውን ቀየረ::

ዘወርዋራ ቅ ጠመዝማዛ፤ ቀጥተኛነት የሌለው::

ዝውውር ስ ቅያሬ፤ ልውውጥ፤ እንቅስቃሴ::

ተዘዋወረ ግ 1. ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ሄደ:: 2. ተለዋወጠ፤ ተቀያየረ:: 3. ተሿሿረ፤ ተጠማዘዘ (ቦታውን ለቆ):: 4. ወዲያና ወዲህ ሄደ፤ ዞረ::

ተዘዋዋሪ ቅ 1. ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ የሚሄድ፤ ተንቀሳቃሽ፤ ዟሪ:: 2. ቋሚ አድራሻ የሌለው:: *ተዘዋዋሪ ነጋዴ*::

በተዘዋዋሪ ተው.ግ. 1. በሌላ ሰው አማካኝነት፤ በእጅ አዙር:: 2. በሌላ አባባል:: 3. ስልክ ደዋዩ ሳይሆን የተደወለለት ሰው ሂሳቡን የሚከፍልበት የስልክ ጥሪ::

ተዛወረ ግ 1. ተቀየረ፤ ተለወጠ:: 2. ተላለፈ፤ ተጋባ (በሽታ):: 3. ወደ ሌላ ቦታ ተመደበ (ለስራ፣ ለኑሮ):: 4 ከአንድ ደረጃ ወደሌላ ደረጃ፤ ከክፍል ወደክፍል አለፈ፤ ተሸጋገረ (ለተማሪ)::

ተሿሿረ ግ 1. ወዲያና ወዲህ አለ፤ ተንቀሳቀሰ:: 2. ተቀያየረ፤ ተለዋወጠ ::

ተሿሿሪ ቅ 1. ቋሚ አድራሻ የሌለው:: *ተሿሿሪ ነጋዴ*::2. ተቀያያሪ::

አዘዋወረ ግ 1. አቀያየረ፤ አለዋወጠ:: 2. ወደ ሌላ ስራ፤ ስፍራ መደበ:: 3 ወዲያ ወዲህ ወሰደ፤ አንቀሳቀሰ፤ አጓጓዘ:: 4. አቀያየረ::

አዛወረ ግ 1. ቀየረ፤ ለወጠ:: 2. አስተላለፈ (በሽታን):: 3. ወደ ሌላ ስራ መደበ፤ ክፍል አሳለፈ ::

አዞረ ግ 1. አሽከረከረ፤ ጠመዘዘ:: 2. ጠመጠመ:: 3. አንቀዋለለ፤ አንከራተተ:: 4. አሄደ፣ አበራየ:: 5.አጥወለወለ፤ አመመ (ራስን):: 6. ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ወሰደ:: 7. አቅጣጫ ቀየረ፤ አስቀየረ:: 8. አስተላለፈ፤ አሻገረ:: *በጀቱን አዞረ*::

አዙሮ አየ አመዛዘነ፤ አስተዋለ::

አዞረበት 1. አምታታበት፤ ግራ አጋባው:: 2. መተት አደረገበት::

ማዞሪያ ስ 1. ከቅል ወይም ከቆርቆሮ የሚሰራና ሊጥን ምጣድ ላይ በክብ ቅርፅ እያሰፉ ለመጋገር የሚያገለግል እቃ:: 2. ከተለያዩ ቦታዎች የሚመጡትን የስልክ ጥሪዎች በመቀበል

ከሚፈለገው መስመር ጋር የሚገናኙት ስራ የሚካሄድበት የስልክ ክፍል። 3. የትራንስፖርት መስመር መነሻ፥ መድረሻ፥ መታጠፊያ።

ኣዙሬት ስ 1. በወራጅ ውሃ ወይም በወንዝ ላይ ክብ እየሰራ የሚሽከረከር ውሃ። 2. ኣእምሮ የሚያስት፥ የሚጥል በሽታ ።

ኣዟሬ ስ የሚሸጡ እቃዎች በመያዝ ወዲያና ወዲህ እየተዘዋወረ የሚሸጥ ነጋዴ ።

ኣዟዟረ ግ ኣለዋወጠ፡ ኣቀያየረ።

ዞግ ስ ወገን፡ ነገድ ።

ዞፍ ስ1. ከእንግዴ ልጅ ጋር የሚወጣ ሽል የተጠቀለለበት ልፋጭ መሰል ነገር። 2. የማዝማ ማር ሽፋን። 3. በእንቁላል ውስጥ በእስኳሉ ዙሪያ የሚገኝ ነጭ ዝልግልግ ፈሳሽ።

ዞዼ(ዞዺ) ስ በበረሃ የሚበቅል፥ እንጨቱ ጥቁርና ጠንካራ የሆነ የእፀዋት ኣይነት።

ዟ[1] የ"ዘ" ፈደል ፍንፅቅ ዘር።

ዟ[2]

ዟ ብሎ ተኛ ተዘርግቶ፡ ተመቻችቶ ተኛ።

ዟ ብሎ ወደቀ በቁመቱ፥ እንዳለ ዘፍ ብሎ ወደቀ ።

ዟሬ "ዞረ" ስር ተመ.

ዠ

ዠ ከ"ዘ" ፊደል ዘር ቀጥሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል (ግእዙ ሆሄ)።

ዠለቴ "**ጀለቴ**"ን ተመ.

ዠለጠ(ጀለጠ) ግ1. በዱላ መታ (ወደ ጀርባ፡ ቂጥ ወይም ጎን አካባቢ)። 2.አለፋ(ለምሳሌ ልብሱን አዘውትሮ በመልበስ፡ያልተሰፋ ቆዳን በእግር በመርገጥ፡...)።

ዠመገገ ግ ሸመጠጠ፡ ፍሬ የተሸከመውን ዛላ በመዳፉና በጣቶቹ መሃል አስገብቶ ወደታች በመሳብ፡በመጎተት (በማለብ አይነት) ፍሬውን እየለየ አራገፈ፡ ወሰደ።

***ዠሞለሞለ**

ዥሙልሙል ቅ ሞላላ ቅርፅ ያለው።

ተዥሞለሞለ ግ 1. ሞላላ ቅርፅ ያዘ። 2. ተንጎለጎለ (ዱቢ)።

አዥሞለሞለ ግ ሞላላ አደረገ።

***ዠረረ**

ዠረር አለ ግ በብዛት ፈሰሰ፡ ወረደ።

ዠረር አደረገ ግ በብዛት አፈሰሰ፡ አወረደ።

ዠረገደ¹ ግ መታ፡ደበደበ።

ዠረገደ² ግ ፈለፈለ ፡ብዙ ወለደ።

ዠረገደ³ ግ አረዘመ።

ዠርጋዳ ቅ ቁመቱ ትልቅ የሆነና የሚያምር ፣ መሰሉ።

ተዠረገደ ግ ቁመታም ሆነ።

ዠረገገ(ጀረገገ) ግ ዠመገገ፡ ሸመጠጠ (ፍሬፍሬን ከዛፍ ላይ)።

ዥርግግ አለ ግ በብዛት አረፈ፡ ፍሬው ተንጠለጠለ።

ተንዠረገገ ግ በብዛት ተንጠለጠለ (ፍሬፍሬ፡...)።

አንዠረገገ ግ በብዛት አንጠለጠለ። *ጌጣጌጥ ነገሮች አንገቷ ላይ አንዠርግጋለች/ወይኑ ተንዠርግጓል።*

ዠርባ "**ጀርባ**"ን ተመ.

***ዠቀዠቀ**

ዠቅዠቃ ቅ በብዛት የሚያፈስ።

ተንዠቀዠቀ ግ 1. በብዛት ወረደ፡ ፈሰሰ (ፈሳሽ)። 2. ተርበደበደ፡ ፈራ፡ ራደ።

አንዠቀዠቀ ግ 1. በብዛት አወረደ፡ አፈሰሰ (ፈሳሽን)። 2. አርበደበደ፡ አስፈራራ፡ አራደ።

***ዠበረረ**

ዠብራራ(ጀብራራ) ቅ 1. ነሁላላ፡ ነገሮችን ልብ ብሎ የማያስተውል ። 2. ሰካራም።

ዥብርር አለ ግ 1. በጣም ተንዠባረረ። 2. ሰከረ።

ዥብርር አደረገ ግ 1. በጣም አንዠባረረ። 2. በጣም አሰከረ።

ተንዠባረረ ግ 1. ነሆለለ፡ ነገሮችን ልብ ብሎ የማያስተውል ሆነ ። 2. በጣም ሰከረ።

አንዠባረረ ግ 1. አነሆለለ፡ አጃጃለ። 2. በጣም አሰከረ።

ዠበበ ግ ሸለብ አደረገ፡ ዘመመ።

ዠበብ አደረገ ግ ሸለብ አደረገ፡ አንቀላፋ።

***ዠበበ**

ዠባባ ስ የሚንዠበብ(አሞሌ፡...)።

ተንዠበበ ግ ተዘረጋ፡ ተንሳፈፈ(በክንፍ...)።

ዠበበ ግ ክንፉን ዘረጋ፡ ወጠረ።

ዠበደ(ጀበደ) ግ ዠለጠ።

ዠበድ አደረገ ዝ.ከ.

ዠብራራ "***ዠበረረ**" ስር ተመ.

ዠብዱ(ዠብድ) "**ጀብዱ**"ን ተመ.

ዠተሬ "**ዦተሬ**"ን ተመ.

ዠንዲ "**ጀንዲ**"ን ተመ.

***ዠወለለ**

ዠውላላ ቅ ጉትት፡ ረዥም ።

ዥውልል አለ ግ ተንዠዋለለ ።

ተንዠዋለለ ግ ተጎተተ፡ ወደጎን ረዘመ ።

አንዠዋለለ ግ ጎተተ፡ አረዘመ።

ዠውጃዋ "**ጀውጃዋ**"ን ተመ.

ዠገዠገ¹ ግ የፍየል የበግ አንጀትን ፡ጅማትን አከረረ (ለክራር፡ ለደጋን)።

ዠገዠገ² ግ አለመጠን ረዘመ፡ ቅጥ ቢስ ሆነ።

***ዠጎረጎረ**

ዥጉርጉር ቅ ዝጉርጉር፡ ቡራቡሬ፡ ነብርማ ።

ተዥጎረጎረ ግ ተዝጎረጎረ፡ በተለያዩ ቀለማት ቀለመ ።

አዥጎረጎረ ግ አዝጎረጎረ፡ በተለያዩ ቀለማት አቀለመ፡ ሸለመ ።

ዠጠዠጠ ግ ገጠገጠ፡ በብዛት ተከለ፡ ደረደረ።

ዡ የ"ዠ" ፊደል ካእብ ዘር ።

ዢ የ"ዠ" ፊደል ሳልስ ዘር ።

ዣ የ"ዠ" ፊደል ራብእ ዘር ።

ዠንደረባ "ጃንደረባ" ን ተመ.

ዠንጥላ "ጃንጥላ" ን ተመ.

ዠገረ ግ አንስቶ ያዘ ፤ ተሸከመ።

ዠግሬ ስ 1፡ የሚሸከም። 2. መሳሪያ ይዞ ጀላ ጀላ የሚከተል ሎሌ።

ዤ የ"ዠ" ፊደል ሃምስ ዘር ።

ዥ የ"ዠ" ፊደል ሳድስ ዘር ።

ዥሙልሙል "*ዠሞለሞለ" ስር ተመ.

ዥማት "ጅማት" ን ተመ.

ዥምብዥብ ስ ወሳንሳ፣ በመተባበር በትከሻ የሚያዝ ሸክም ማንጠልጠያ ።

ዥረት "ጅረት" ን ተመ.

ዥራት "ጅራት" ን ተመ.

ዥብራ "ጅብራ" ን ተመ.

ዥንፎ "ጅንፎ" ን ተመ.

ዥጉርጉር "*ዠጎረጎረ" ስር ተመ.

ዥዋዥዌ "ጅዋጅዌ" ን ተመ.

ዥው "ጅው" ን ተመ.

ዥግራ "ጅግራ" ን ተመ.

ዦ የ"ዠ" ፊደል ሳብእ ዘር።

ዦተሬ(ዦቶሬ÷ጆተሬ) ስ ራሰ ብቻን የዘንጋዳ ሰብል አይነት።

ዧ^{1} የ "ዠ" ፊደል ፍንፅቅ ዘር።

ዧ^{2}

ዧ ብሎ ዘነመ በሃይል ዘነመ።

ዧ ብሎ ፈሰሰ ግልብጥ ብሎ ፈሰሰ።

ዧ መንዧለለ ግ 1.እንደልቡ ሆነ።2.በጥፍ ሰጠ፤ ቸረ።

የ

የ ከ "ሀ" ፊደል ዘር ተተርሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል [illegible] ሆሄ ።

የ— 1. [illegible] የሚያያዝበት ወይም [illegible] የሚያገለግል ቅጥያ [illegible] ለመመስረት የሚያገለግል ምእላድ። *[illegible]* 2. ከ—የመጣ፡ የተገኘ፡ በ—ውስጥ የተሰራ፡ የተመረተ ለማለት የሚያገለግል። *[illegible]* 3. በ—የተሰራ፡ የተደረገ፡ [illegible] ወይም [illegible] *[illegible]* 4. በ [illegible] የሚገኝ፡ የሚኖር [illegible] *[illegible]* 5. [illegible] የሚያመለክት [illegible] *[illegible]* 6. ከ የተሰራ [illegible] ለማለት የሚያገለግል። *[illegible]* 7. [illegible] የሚያገለግል [illegible] *[illegible]* 8. [illegible] ለማለት የሚያገለግል። *[illegible]* 9. በ—ላይ [illegible] ለማለት በቀል መልክ ለመግለፅ ወይም በመስተአምርነት የሚያገለግል። *[illegible]* 10. በ—[illegible] መልክ [illegible] ለማለት ወይም [illegible] ለመመስረት የሚያገለግል። *[illegible]* 11. ስ [illegible] *[illegible]* ...

የሰ ግ አለመኖርን ለመግለፅ የሚያገለግል የአሉ [illegible] አሉታዊ ለማለት [illegible] ለመግለፅ የሚያገለግል። *[illegible]* በሚያስር [illegible] ... [illegible] ... እያለ ይዘረዘራል። [illegible] አንተ [illegible] ...እያለ ይዘረዘራል።

የሰሽ ____ [illegible] ለማለት የሚያገለግል። *[illegible]* ።

የሰሙ አገሮች "ሰማ" ስር ተመ.

የሳም ጨው "ሳም" ስር ተመ.

የሱማሊ እሸት "ሱማሊ" ስር ተመ.

የሉስ ስ [illegible] አንገቱ ግዙፍ የእምራ አይነት።

የምር "መረረ" ስር ተመ.

የምስራች "ምስራች" ስር ተመ.

የብስ ስ በባሕር ውሃ ያልተሸፈነው፡ ውቅያኖስ ያልሆነው፡ ደረቅ የመሬት ክፍል።

የቦ ስ ትንሽ ወፍ ።

የተፀውኦ ስም ስ ሰዎች፡ ስፍራ፡ ድርጅት፡ ሃገር፡... የሚጠሩበትና ተለይተው የሚታወቁበት ስም።

የት ተው.ስ. አቅጣጫን፡ ቦታን ለማወቅ የሚቀርብ መጠይቅ።

የቱ (የትኛው) ተው.ስ. ማንነትን፡ አንዱን ከሌላው ለይቶ ለማወቅ ለመጠየቅ የሚያገለግል ቃል። *ስራ አስኪያጁ የቱ ነው?*

የትም የት የትም ቢሆን፡ በማንኛውም ቦታ። *የትም የት ብትሄድ አታመልጠንም።*

የትና የት ... አይመጣጠንም፡ ይለያያል ለማለት የሚያገለግል ቃል። *እዚህ የሚሸጠውና እዚያ የሚሸጠው የትና የት፡ አይገናኝም።* 2. በጣም ሩቅ ለማለት የሚያገለግል። *ቤቱ ቅርብ እንዳይመስልህ የትና የት ነው።*

የትየለሌ(የት እየለሌ) በጣም ሩቅ ወይም በጣም ብዙ ለማለት የሚያገለግል አባባል።

የኔ ቢጤ "እኔ" ስር ተመ.

የኔታ(የኔታ) ቅ [illegible] መምህር፡ አስተማሪ ለማለት የሚያገለግል የአክብሮት አጠራር ።

የአዋጅ ዋስ^{1} ስር ተመ.

የኩቴት ስ [illegible] የሚመጣ የአመጋ [illegible] ስም ።

የኮት "ኮተተ" ስር ተመ.

የወል "ወል" ስር ተመ.

የዋህ ቅ 1. ገር፡ ቅን። 2 ሞኝ፡ ተላላ ።

የዱ ስ ተኩላ ።

የጉድፍ "ጎደፈ" ስር ተመ.

የፈጥኝ "ፈጥኝ" ን ተመ.

ዩ የ"የ" ፊደል ካእብ ዘር ።

ዩራኒየም ስ የአቶሚክ ሃይልን ለማመንጨት የሚያገለግል የማእድን አይነት ።

ዩኒቨርሲቲ ስ ከፍተኛ ትምህርት በዲግሪ ደረጃ የሚሰጥበት የትምህርት ተቋም ።

ዩኒፎርም ስ በአንድ አይነት የስራ መስክ የተሰማሩ ሰዎች ወይም በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ

የሚማሩ ተማሪዎች ከሌላው እንዲለዩበት ታስቦ የሚለብሱት አንድ አይነት ስፌትና ቀለም ያለው ልብስ።

ዪ የ"**የ**" ፊደል ሳልስ ዘር።

ያ¹ የ"**የ**" ፊደል ራብዕ ዘር።

ያ² (ብ.ቁ. እኒያ፣ እነዚያ፣ እነዚ፣ እነ.ያ.ያሉ) የሩቅ አመልካች ተውላጠ ስም። *ያ መጽሃፍ የኔ ነው።*

—ያ (—ኢያ) በአርእስቱ የተ ስሞች መድረሻ ላይ እየተቀጠለ አንድ ነገር የሚፈፀምበትን ጊዜ ቦታ፣ መሳሪያ፣ ዘዴ… የሚያመለክት የማድረጊያ ስሞችን ለመመስረት የሚያገለግል ምእላድ (ለምሳሌ፣ መቀረጫ መጥረጊያ መስበር መስበርያ)።

ያህል(ያክል) "**አክለ**" ስር ተመ.

ያለ— "**አለ—**" ን ተመ.

ያለበለዚያ "**አለበለዚያ**" ን ተመ.

ያለዚያ ዝ.ክ.

ያመራማሪ "***መረመረ***" ስር ተመ.

—ያን —ዊ ን በመቀጠል በተመሰረቱ ቅፅሎች ላይ እየገባ የስም ቁጥር ስምን ለመመስረት የሚያስችል ምእላድ (ለምሳሌ፣ ኢትዮጵያዊ ኢትዮጵያውያን ዘማዊ ዘማውያን)።

ያዘ ግ 1. ለተም አፈና አደረገ፣ በእጅ አሰረ፣ ጨበጠ። 2. ተሸከመ፣ አነሳ፣ ታቀፈ። 3. አቆረ፣ ቋጠረ። *መንገድ ያዘ።* 4. ቻለ፣ አካተተ። *እንስራው ሁለት ጋን ውሃ ያዛል።* 5. በቁጥጥር ስር አዋለ። *ወንጀለኛ ያዘ/ ሌባ ከተማውን ያዘ።* 6. አቆመ፣ አገደ፣ እንዳይሰራ፣ እንዳይሄድ አደረገ። *ሰሞሬ ያዘኝ።* 7. ማቀጣጠል ማቃጠል ማፍራት… ጀመረ። *ብርቱካኑ ይዟል።* 8. አንድን የተወሰነ ድርጊት በማከናወን ላይ ሆኖ ተሰማራ። *ወሬ ያዘ/ ስራ ያዘ።* 9. ንብረትን ገንዘብን ወይም ሌላ ነገርን አኖረ አስቀመጠ። 10. በአእምሮው መዘገበ፣ አስታወሰ… በእጁ ያለውን በእጁ አደረገ። *ገንዘብ ይዟል። መታወቂያ ይዟል።* 11. ከ—ጋር አብሮ ሆነ። *ልጆቹን ይዞ ሄደ/ ሰው ይዞ እከራከራለሁ።* 12. አላመመ። *ጉንፋን ያዘው።* 13. እጁን በአንድ ነገር ላይ አሳረፈ። *መዝሙር ይዞ ቆመ/ በመንገዱም ራሱን ያዘ።* 15. በአንድ አይነት ደረጃ፣ ሁኔታ… ተገኘ። *የአንደኛነትን ደረጃ ያዘ።* 16. አደረገበት። *ፍርሃት ያዘው።*

ያዘች ግ ፀነሰች፣ አረገዘች።

ያዝ ለቀቅ አደረገ ግ 1. አጥብቆ ሳይከታተል ቀረ፣ ተዳከመ። 2. አንድ ጊዜ ጠንክሮ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሁለም ተሰማ።

ይዞህ ይሂድ(አነ.) ለሞት ይዳርግህ።

መያዣ ስ 1. እጀታ መጨበጫ። 2. እቃ መያዣ፣ ማስቀመጫ፣ መቋጠሪያ፣ ከረጢት… 3. እንደዋስትና የሚያገለግል እቃ፣ ገንዘብ። 4. ከሰው ብድር እንደሚፈ ስር ተይዞ የሚቀመጥ የቅድሚያ ወይም የዋስር ወለድ እንደሚፈ።

ይዘት ስ 1. በአንድ ነገር ውስጥ ያለው የሚገኝ ነገር፣ የተያዘ። 2. በአንድ ፅሁፍ ውስጥ የሚገኝ ሀሳብ ጉዳይ፣ መልእክት… 3. በአንድ ነገር ያረጋ የሆነ ምልክት ምልክቱ… ነው።

ይዞታ ስ 1. በንብረትነት ያለ እቃ፣ ንብረት… በዘመን ጊዜ መሬት። 2. አቋም፣ ሁኔታ…

ተያዘ ግ 1. በጉልበት ወይም በሀብት ቁጥጥር ስር ዋለ፣ ታሰረ። 2. ያመለጠ የሸሸ… ሰው ወይም እንስሳ በቁጥጥር ስር ዋለ፣ እጅ ገባ። 3. በቁርማይ ለመጣ ሰው ወይም በሌላ ሁኔታ ቢገባው፣ መቀመጫ… እ ተያዘ… ለሌላ ተቀመጠ ተከለለ፣ ቀረ። *በትያትር ቤቱ ወንበር ተያዘላት።* 4. ተለከፈ በበሽታ… 5. ተጠመደ በስራ… 6. በመያዣ መልክ ተቀመጠ እቃ ገንዘብ… ።

ተያዥ ስ ዋስ፣ አንድ ሰው ቃሉን ቢያፈርስ ለሰጠው ተጠያቂ ለመሆን በፈቃደኝነት ሃላፊነቱን የሚወስድ ሰው።

ተያያዘ ግ 1. ተገናኘ፣ ተቆላለፈ፣ ተጣመረ፣ 2. ተተሳሰረ፣ ጎደኛ ሆነ… 3. ተጣመደ፣ ተጣላ… 4. ተናነቀ… 5. ፊር ያዘ፣ ተጀመረ፣ በመከናወን ላይ ሆነ…

አያያዘ ግ 1. አገናኘ፣ አቆላለፈ… 2. አጣላ። 3. አገዘ ስራው እንዲጀመር አደረገ። 4. አጣበቀ፣ አቆላለፈ፣ አሳተሰረ። 5. ፊት አገዘ…

አያያዝ ስ የስራ አፈፃፀም፣ አንድን ደርገ የሚከናወንበት ሁኔታ፣ አኳኋን… ። *አያያዙ አያምርም እንደአያያዙ ቢሆን ሊፈፀም ቀሎ ይወለደሀል።*

አያያዥ ቅ አጣዳኝ፣ ነገረኛ።

አስያዘ ግ 1. በቁጥጥር ስር እንዲሆን አደረገ። 2. አንድን እቃ፣ ገንዘብ በመያዣ ሰጠ።

ዬ የ"**የ**" ፊደል ሃምስ ዘር።

—ዬ "**—ኤ**" ን ተመ.

ይ የ"**የ**" ፊደል ሳድስ ዘር።

ይህ(ብ.ቁ. **እነዚህ/እኒህ**፣ አን.ፆ. **ይቺ**) የቅርብ አመልካች ተውላጠ ስም ወይም ቅፅል። *በሬው መርጌ ይህ ነው፤ ይህ በሬዬ ስራ ነው።*

ይሆናል "**ሆነ**" ስር ተመ.

ይለይለት "**ለየ**" ስር ተመ.

ይሉኝታ "**አለ**" ስር ተመ.

ይሉኝ አይል ዝ.ክ.

ይልቅ **"ላቀ"** ስር፡ ተመ.

ይሙት በቃ **"ሞተ"** ስር፡ ተመ.

ይርጋ **"ረጋ"** ስር፡ ተመ.

ይቅርታ **"ቀረ"** ስር፡ ተመ.

ይበል **"አለ"** ስር፡ ተመ

ይብላኝ **"በላ"** ስር፡ ተመ.

ይቶት ስ መነኩሲት ወይም አሮጊት የምትጠራበት ስም፤ እማሆይ።

ይድረስ **"ደረሰ"** ስር፡ ተመ.

ይግባኝ **"ገባ"** ስር፡ ተመ.

ይፋ ቅ ገሃድ፤ ግልፅ።

በይፋ በገሃድ፤ በግልፅ።

ይፋ ወጣ 1. ሁሉም እንዲያውቀው ተደረገ፤ ተነገረ። 2. ታየ፤ ተገለጠ።

ዮ የ"**ዮ**" ፊደል ሳብእ ዘር።

—ዮሽ አንድ ነገር ስንት እጅ፤ የስንት ወገን፤ የምን ወገን እንደሆነ ለማሳየት ከቁጥር በስተመጨረሻ የሚገባ ምእላድ። *ሁለትዮሽ/ ሦስትዮሽ*።

ዮጋ ስ የራስ ፍልስፍና አስተምህሮ ያለው የሂንዱ ስፖርታዊ የሰውነት እንቅስቃሴ።

ደ

ደ ከ "ዮ" ፊደል ዘር ቀጥሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል (ግእዝ ሆሄ)።

ደሀየ ግ ተቸገረ፣ ለኑሮ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን አጣ።

ደሃ (ድሃ) ቅ 1. ችግረኛ። ስ 2. በቂ መተዳደሪያ የሌለው ሰው። 3. ለማኝ።

ደሃ ንቀል ስ የአረም አይነት፣ አቀንጭራ።

የደሃ አባት ስ ለደሃ የሚያዝን፣ ደሃን የሚረዳ፣ ቸር፣ ለጋስ ሰው።

ደሃ አደግ ቅ እናት አባቱ የሞቱበት፣ በችግር ያደገ።

***ደሃረ**

ደሃራ-ዪ(ደሃራ፥ዳህራ-ዪ፥ዳራ) ስ በስተኋላ ያለ የከርቤ ላይ ድጋፍ፣ መደገፊያ(ስእሉን ከርቤ ስር ተመ.)።

ድህረ ___ ከ__ በኋላ፣ የ "ቅድመ__" ተቃራኒ። *ድህረ ወሊድ፣ድህረ አብዮት።*

ድህረ ምረቃ ስ ከመጀመሪያ ዲግሪ በኋላ የሚሰጥ የትምህርት መርሃ ግብር።

ደህና ቅ 1. ጥሩ፣ መልካም። 2. ሰላም፣ ጤና። *ደህና ነህ ?*

ደህንነት ስ 1. በጥሩ፣ በመልካም ሁኔታ ላይ መሆን። 2. ጤንነት። 3. የአንድን አገር ህዝብ ሰላም፣ ፀጥታ፣ ጥቅም... ለማስከበር ተግባራዊ ሁኔታዎችን በምስጢር የሚከታተልና መረጃዎችን የሚሰበስብ (ሰው ወይም ድርጅት)፣ ነፍሰ ሰባሽ፣ ሰላይ።

ደለሀ ግ ድልህ አዘጋጀ።

ድልህ ስ 1. ተፈጭቶ በውሃ የተላቆጠ በርበሬ። 2. የተፈጨ በርበሬ።

ድልህ መሰለ ቀላ፣ በርበሬ መሰለ።

ደለለ¹ ግ አባበለ፣ሸነገለ፣ አሞኘ፣ አታለለ።

መደለያ ስ መሸንገያ፣ ማባበያ።

ደላይ ቅ ሸንጋይ፣ አታላይ።

ድለላ ሽንገላ።

ድልል ቅ በቀላሉ የሚታለል፣ የሚሸነገል።

ተደለለ ግ ተሸነገለ፣ ተታለለ።

ደለለ² ግ ገንዘብ እየተከፈለው ተፈላጊዎችን (ሻጭና ገዥን፣አከራይና ተከራይን...) አገናኘ፣ አስማማ።

ደላላ ስ 1. በመደለል ስራ ላይ የተሰማራ ሰው። ቅ 2. አታላይ፣ በውሸት አማባብቶ ለማሳመን የሚሞክር።

ድለላ ስ ተፈላጊዎችን የማገናኘት፣ የማስማማት ስራ።

ድላል ስ ለደላላ የሚከፈል ገንዘብ።

ደለለ³ ግ ቆለለ፣ ከመሬት (ወንዝ አፈርን አሸዋን...)።

ደለል ስ ከበረዶ በኋላ በወንዝ ወይም በጎርፍ ተሸክሞ ተጠርጎ ሌላ ቦታ የሚከመር አፈር፣ አሸዋ...።

ደለሳም ቅ ብዙ ጊዜ ደለል የሚገኝበት ቦታ።

ደለመ ግ 1. ወሰለመ፣ ጨለመ። 2. ጠፋ፣ ተደመሰሰ (አይን፣ ስለት፣ ቅርጽ...)።

ደለማ ስ ጨለማ።

ደላማ ቅ ለምጣድ አይን የሌለው እንጀራ።

ደለመጠ ግ ወፈረ፣ ፈረጠመ።

ደልማማ ቅ ፈርጣም፣ ደለ ወፍራም።

ድልምጥ ዘ.ከ.

አደለመጠ ግ ወፈረ፣ ፈረጠመ።

ደለማ "ደለመ" ስር ተመ.

ደለሰ ግ 1. ቀባ፣ ለበጠ (ቅቤን...)። 2.አስተኛ፣ መጠለስ ሁኔታን። 3. ጠፈጠፈ፣ ደለሽ አበጀ።

ደለሽ ስ የተለያዩ የእህል አይነቶችን በአንድ ጎተራ ውስጥ እያንዳንዱ ለማስቀመጥ ሲያስፈልግ፣ አንዱ አይነት እህል ከሌላው ጋር እንዳይቀላቀል በየመካከላቸው የሚደረግ ሰፌድ መሰል የጭቃ ጥፍጥፍ።

ደለቀ ግ 1. ደቀ፣ ገሰመ፣ መታ። 2. ዘለለ፣ ጨፈረ።

ድለቃ(ድልቂያ) ስ ጭፈራ።

ተደለቀ ግ ተጨፈረ።

ደለቀቀ ግ ዘቅ አለ (ውሃን፣ግንድን...)።

***ደለቀቀ**

ደለቀቅ(ዴሊቃቃ) ቅ 1. ቅምጥል፣ የደላው፣ ቀብራራ። 2. ምልቅቅ።

ድልቅቅ አለ ግ ተንደላቀቀ።

ድልቅቅ አደረገ ግ አንደላቀቀ።

ተንደላቀቀ ግ 1. ተቀማጠለ፣ተንቀባረረ። 2. ተምላቀቀ።

አንደላቀቀ ግ 1. አቀማጠለ፣ አንቀባረረ። 2. አምላቀቀ።

ደለበ ግ 1. ለብዙ ጊዜ ተቀመጠ፣ ተከማቸ፣ ተከዘነ፣ ተጠራቀመ። 2. ሸገተ፣ ዘር ተከማችቶ ብዙ ጊዜ ከመቀመጡ የተነሳ። 3. ወፈረ፣ ሰባ።

ድልብ ቅ 1. የሰባ፣ በተለይም የወፈረ(ከብት)። 2. በብዛት ተከማችቶ ብዙ ጊዜ የተቀመጠ።

ደለንቲ (ደለንቲ) ቅ ደንዝ፣ፈዛዛ።

ደለዘ¹ ግ ሰረዘ፡ አጠፋ፡ ደመሰሰ (ፅሑፍን በቀለም)።

ድልዝ ቅ 1. ስርዝ። 2. ፊት የነበረው ፅሑፍ ተፍቆ ወይም ቅርፁን እንዲለውጥ ተደርጎ በላዩ ላይ ሌላ ሃሳብ የሰፈረበት (ፅሑፍ)።

ተደለዘ ግ ተሰረዘ፡ ጠፋ፡ ተደመሰሰ(ፅሑፍ)።

ደለዘ² ግ 1. መታ፡ ደለቀ፡ ነረተ። 2. በርበሬን ከሽንኩርት፡ ከዝንጅብል፡ ከጨው፡... ጋር በማደባለቅ አብሮ ወቀጠ።

ድልዝ ቅ ከሽንኩርት፡ ከዝንጅብል፡ከጨው፡... ጋር አብሮ የተወቀጠ(በርበሬ)።

ደለይ[ንፋስ] ስ በጥር ወር የሚወጣ የኮከብ አይነት፡ በተጨማሪ "**ኮከብ ቆጠራ**"ን ተመልከት።

ደለደለ ግ 1. አስተካከለ፡ አመቻቸ። 2.መደበ፡ ከፋፈለ። 3. ወፈረ፡ ፈረጠመ። 4. ድልድይ ሰራ፡ አበጀ። 5. ከተረ፡ ገደበ (ውሃን በፈርና በድንጋይ)።

ድልዳል ስ 1. ለመኝታ፡ ለመቀመጫ እንዲመች ሆኖ የተዘጋጀ ትግትግ፡ ምንጣፍ። 2. በጭነት ከብት ጀርባ ላይ ከጭነቱ ስር የሚደረግ ትግትግ፡ መደላድል።

ድልድይ ስ በወንዝ ወይም በወንዝ ቅርፅ ባለው መሬት ላይ ከእንጨት፡ ከድንጋይ፡ ከብረት፡... የሚሰራ መሻገሪያ ፡ መሸጋገሪያ።

መደላድል ስ ድልዳል።

ተደለደለ መደላድል ተበጀ፡ ትግትግ ተደረገ።

ደልዳላ ቅ 1. አባጣ ጎባጣ የሌለበት፡ የተስተካከለ (ቦታ፡ መሬት፡...)። 2. የተመጣጠነ አካላዊ አቋም ያለው(ሰው)። 3. (ዘይ.) በእድሜና በአስተሳሰብ የበሰለ።

ድልድል ቅ የተደለደለ፡ የተስተካከለ (መሬት)።

ድልጅል ስ 1. ክፍፍል። 2. ምድብ፡ ምደባ።

ድልጅል አለ ግ በጣም አበጠ (ሰውነት በህመም ምክንያት)።

ተደላደለ ግ 1. ተከፋፈለ። 2. (ዘይ.) ረጋ፡ ተመቻቸ (በኑሮ፡...)።

አደላደለ ግ 1. አከፋፈለ፡ 2. አመቻቸ፡ አስፈላጊውን አሟላ።

ደለፈሰ ግ 1. አፈሰ፡ ዛቀ። 2. ጨፈለቀ፡ ረገጠ (ጭቃን፡...)።

ደላ ግ ተመቸ፡ ተስማማ።

ድሎት ስ ምቾት።

ተድላ ዝ.ከ.

***ደላ**

አደላ ግ 1. አድልዎ ፈፀመ። 2. ወደ አንድ ፊት፡ በኩል፡ አቅጣጫ፡ ወገን፡... አጋደለ፡ ሰገጠ፡ ረዘመ፡ ዘዘ... ።

አዳላ ግ አደላ ።

አድልዎ(መድሎ) ስ ደሀውን ብሎ አንዱን ወገን በመንዳት ሌላውን ወገን የመጥቀም ዝንባሌ፡ ድርጊት ።

ደላላ "**ደለለ²**" ስር ተመ.

ደላማ "**ደለመ**" ስር ተመ.

ደላይ "**ደለለ¹**" ስር ተመ.

ደላን ስ 1. ድብዳብ፡ የበግ ቆዳ። 2. የቁርበት፡ የነት እላቂ። 3. (ዘይ.፡ ስድብ) ቂል፡ ሞኝ።

ደልማማ "**ደለመጠ**" ስር ተመ.

ደልቃቃ "***ደለቀቀ**" ስር ተመ.

ደመለለ ግ ጠቀለለ፡ ሸመለለ።

ተደመለለ ግ ተጠቀለለ፡ ተሸመለለ።

ደመመ ግ አፈር አለበሰ፡ በአፈር ሸፈነ።

መደምደም(መደንን) ስ ድፋር፡ አስከሬኑን አፈር እንዳይነካው ከጉድጓዱ አፉ ዝቅ ብሎ የሚደረግ ርብራብ፡ ግጣም።

***ደመጠ**

ተደመመ ግ 1. ተደነቀ፡ ተገረመ። 2. ዝም አለ፡ ፀጥ አለ።

አስደመመ ግ አስደነቀ፡ አስገረመ ።

ደመረ ግ 1. ሰበሰበ፡ አከበ፡ አከማቸ፡ ቆለለ። 2. አንድ ላይ አጠቃለለ (የተለያዩ ነገሮችን፡ ቁጥሮችን፡...)። 3. ደመራ ሰራ፡ አበጀ።

መደመር ስ ከአራቱ የስሌት መደቦች አንዱ የሆነና ልዩ ልዩ መጠን ያላቸውን አሃዞች በአንድ ላይ አጠቃሎ የመቀመር ዘዴ።

የመደመር ምልክት ስ የመስቀል ቅርፅ ያለው የስሌት ምልክት፡ ምልክቱም (+) ነው።

ደመራ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ስ 1. መስከረም 16 ቀን የሚከበር የመስቀል በዓል ዋዜማ። 2. ከላይ የተጠቀሰውን በዓል አስመልክቶ በስነ ስርአቱ ላይ እንዲነድ የሚደረግ የእንጨት ቁልል፡ ስብስብ።

ድምር ስ 1. ክምችት፡ ጥቅል። 2. በአንድነት የተሰላ፡ የተቀመረ የብዙ ቁጥሮች ጥቅል ውጤት።

ደመሰሰ ግ 1. አጠፋ፡ እንዳልነበር አደረገ። 2. ገደለ፡ በሙሉ ጨረሰ።

ድምስስ አለ ግ ተደመሰሰ።

ተደመሰሰ ግ 1. ጠፋ፡ ተበላሸ፡ እንዳልነበር ሆነ። 2. ተገደለ፡ ተጨረሰ (ሙሉ በሙሉ)።

ደመቀ ግ 1. ጎላ፡ ቦግ አለ (ቀለም፡...)። 2. ተሟሟቀ፡ ተጋጋለ (ጨዋታ፡ ወሬ፡...)።

3. አማረ፣ ተዋበ፣ ተሸላለመ፡፡ *የሰው ወርቅ አያደምቅ*፡

ደማቅ ቅ 1. የጎላ፣ ቦግ ያለ (ቀለም፣...)፡፡ 2. የሞቀ፣ የተጋጋለ (ጨዋታ፣ ዘፈን፣...)፡፡

አደመቀ ግ 1. አሟሟቀ፣ አጋጋለ (ጨዋታን፣ ወሬን፣...)፡፡ 2. ተለይቶ፣ አምሮ፣ ጎልቶ እንዲታይ አደረገ፡፡

ደመና "ዳመና" ስር ተመ.

ደመኛ "ደማ" ስር ተመ.

ደመወዝ(ደሞዝ) ስ 1. አሰሪው ወገን ለሰራተኛው በየተወሰነ ጊዜ የሚከፍለው የተወሰነ የገንዘብ መጠን፣ የጉልበት፣ የስራ፣ የድካም ዋጋ፡፡ 2. ቀለብ ፡፡

የደመወዝ ጭማሪ ስ ቀድሞ በነበረው ደመወዝ ላይ የታከለ፣ የተጨመረ ገንዘብ፡፡

ደመወዝ ከፋይ ስ ለሰራተኞች ደመወዝ እንዲከፍል የተመደበ ሰራተኛ ፡፡

ደመደመ ግ 1. ደፈነ፣ ተመተመ፡፡ *ቁስሉን በመድሃኒት ደመደመው* ፡፡ 2. ጨረሰ፣ ፈፀመ፡፡ 3. በእጅ እየተጫነ አስተካከለ፣ አበጃጀ፣ ከመከመ (ቡኮን)፡፡

ድምድማት ስ የግንብ ወይም የግድግዳ አናት፣ መጨረሻው፣ ክፈፉ፡፡

*ደመጠ

ድምጥ "ድምፅ" ን ተመ.

ድምጥማጥ በፊደል ተራው ተመ.

ተደመጠ ግ ሰሚ አገኘ፣ ተሰማ፡፡

ተደማጭ ቅ ተሰሚ፣ ሃሳቡ ተቀባይነት ያለው፡፡

ተደማመጠ ግ አንዱ ሌላው የሚለውን ሰማ፡፡

አደመጠ(አዳመጠ) ግ በጆሮው ሰማ፣ ሰምቶ ልብ አደረገ፡፡

አድማጭ ስ ሰሚ፡፡

ደማ ግ 1. ደም ወጣው፣ ደሙ ፈሰሰ፡፡ 2. (ዘይ.) ለሃገሩ፣ ለወገኑ መስዋእትነት ከፈለ፥ ታገለ፡፡

አይደማውም ስስታም ነው፣ አይሰጥም፡፡

ደም ስ 1. በሰው፣ በእንስሳትና በነፍሳት አካላት ውስጥ የሚዘዋወር ቀይ ፈሳሽ፡፡ 2. ወዘና፥ ላህይ፡፡

[ደሙ]ደመከልብ ሆነ በደረሰበት አደጋ የፈሰሰው ደሙ እንደ አልባሌ ነገር በከንቱ ቀረ፣ ብድር መላሽ አጣ (በፈፃሚው የፍርድ ወይም የበቀል እርምጃ ባለመወሰዱ)፡፡

ደሙ ደረቀ በገዳይና በሟች ቤተሰብ መካከል ተፈጥሮ የነበረው ጠብና ቂም በእርቅ አማካኝነት ቀረ፥ ተተወ፡፡

ደሙ ሳይደርቅ የተፈፀመው በደል ሳይቆይ፥ ሳይረሳ፣ በትኩሱ፡፡

ደሙ ፈላ በጣም ተናደደ፡፡

ደም ፍላት ድንገት የሚያጋጥም ሃይለኛ ንዴት፣ ቁጣ፡፡

ደሙን መለሰ/ተወጣ ለተሰነዘረበት ጥቃት ብድሩን መለሰ፣ ተበቀለ ፡፡

ደም መላሽ በሌላ ሰው ላይ የተፈፀመን ግፍ የሚበቀል፣ ብድር የሚመልስ፡፡

ደም መልስ በሰውነት ውስጥ ያለን ደም ወደ ልብ የሚወስድ ትልቅ የደም ቧንቧ፡፡

ደሙን አዘራ ደሙን አፈሰሰ፡፡

ደሙን አፈሰሰ ተዋጋ፥ ተጋደለ፥ መስዋእት ሆነ፡፡

ደም መታት ከማህፀኗ ብዙ ደም ፈሰሳት፡፡

ደም ረገጠ 1. ለጭዳ ተብሎ የፈሰሰ ደም በመርገጡ በበሽታ ላይ ወደቀ፥ ደንቃራ ገባ (አምልኮ)፡፡ 2. ወደ ቤቱ ሲገባ እርድ ታረደለት (አዲስ ቤት ለሚገቡ፣ ለሙሽራ፥...)፡፡

ደም ሸተተው ጠብ፥አምባጓሮ አሰኘው፡፡

ደም ተቃባ /ተጋባ ጠላት ተኳኋነ (በነፍስ ግድያ ምክንያት)፡፡

ደም ተፋ በጣም ደከመ፥ ለፋ፥ ተሰቃየ፥ ጣረ (አንድን ነገር ለማከናወን)፡፡

ደም ተፋሰሰ 1. ደም ተቃባ፡፡ 2. ተጋደለ፡፡

ደም አስተፋው 1. በጣም ደበደበው፡፡ 2.እጅግ በጣም አሰቃየው (ስራ፣...)፡፡

ደም አስተፊ ስ ስሩ ቀይ ቀለም የሚመስል ፈሳሽ ሊወጣው የሚችል የእፅዋት አይነት፡፡

ደም አስተፊት ስ መርዛማ በመሆኑ የማይበላ የእንጉዳይ አይነት፣ ምላስ ጎልጉል፡፡

ደም አፈታበት ደሙ ከመፍሰስ አላቆም አለ፡፡

ደም ደም አለው ቀፈፈው፣ ደስ የማይል ስሜት ተሰማው፡፡

ደም ጎረሰ በደም ተለወሰ፣ ደም ሰረበ፡፡

ደም ጠማው የመግደል ፍላጎት ያዘው፡፡

ደም ጠራው በሄደበት ድንገተኛ ሞት ሞተ፡፡

ደም ፈሰሰ 1. ነፍስ ጠፋ፣ ግድያ ተፈፀመ፡፡ 2. እንደዶሮ፥ በግ ያለ እንስሳ ታረደ፡፡3. ሰው ተፈነከተ፥ቆሰለ፥...፡፡

ደም አፈሰሰ 1. ዶሮ፣ በግ፣... ከቤቱ አረደ፡፡ 2. ሰው ፈነከተ፥ አቆሰለ፥ አደማ፡፡ 3. ሰው ገደለ፥ ነፍስ አጠፋ፡፡

ደም አፋሰሰ አጋደለ፣ መሳሪያ እንዲማዘዙ፥ እንዲጣሉ፥ እንዲመታቱ ምክንያት ሆነ፡፡

ደም አፋሳሽ ቅ ለሌሎች መጣላት፥ መደባደብ፥ መገዳደል ምክንያት የሆነ ወይም

የሚሆን።

ደሟ ቀረ ፀነሰች።

ደሟ ጠራ የወር አበባዋ ቆመ።

ደሟ ፍልቅ ያለ የተዋበች፣ ያማረች።

የደም አበላ ወሰደው ብዙ ደም ፈሰሰው።

ደመ መራራ ቅ የሚናገረውን፣ የሚያደርገውን ነገር ሁሉ ሰዎች በክፉ የሚተረጉሙበት፣ ነገር የሚነግስበት፣ የሚገንበት (ሰው)።

ደመ ሞቃት ቅ ቅንዝረኛ።

ደመ ሞቃት እንስሳት ስ በአካላቸው ውስጥ ያለው ደም ሞቃት የሆነና በየትኛውም የአየር የጠባይና አካባቢ የደማቸው ሙቀት የማይለዋወጥ እንስሳት።

ደመ ቀዝቃዛ ቅ 1. ቅንዝረኛ ያልሆነ። 2. ቶሎ የማይቆጣ፣ ረጋ ያለ።

ደመ ቀዝቃዛ እንስሳት ስ በአካላቸው ውስጥ ያለው ደም ቀዝቃዛ የሆነና በተለያየ የአየር ጠባይና አካባቢ የደማቸው ሙቀት ከፍ ወይም ዝቅ በማለት የሚለዋወጥ እንስሳት።

ደመ ነፍስ(ደማዊት ነፍስ) ስ 1. የእንስሳት ነፍስ። 2. (ስድብ) የማያስብ፣ የማያመዛዝን (ሰው)።

በደመ ነፍስ 1. ባለማመዛዘን፣ ባለማስተዋል። 2. በተፈጥሮ በተገኘ እውቀት የሚያከናውኑት ድርጊት።

ደመ ግቡ ቅ መልከ መልካም፣ ውብ፣ ማራኪ ገፅታ ያለው።

ደም ግባት ስ ውበት፣ ቁንጅና፣ ወዘና።

ደም ቅዳ ስ ከልብ ወደ ሌላው የሰውነት ክፍል የሚሰራጨውን ደም የሚወስድ ትልቅ የደም ቧንቧ።

[የ] ደም ግፊት/ብዛት ስ የሚፈለገው መጠን መሆን ከሚገባው በላይ ከፍ ብሎ በደም ስሮች ውስጥ የሚካሄድ የደም ዝውውር ሂደት፣ በዚሁ የተነሳ የሚፈጠረው ህመምም ደም ግፊት ይባላል።

ደም ጥሬ የወር አበባ የሚቆምበት ጊዜ ወይም እንደቆመ ያለው ጊዜ።

የደም ስር ስ 1. በሰውነት ውስጥ ደም የሚዘዋወርበት ቀጫጭን ቧንቧ። 2. ዋና፣ በጣም አስፈላጊ ነገር። *ቡና ለአገሪቱ ኢኮኖሚ የደም ስር ነው።*

የደም አይነት ስ በሰዎች ደም ንጥረ ነገርና አይነት መካከል ያለውን ልዩነት መሰረት በማድረግ የተከፋፈሉት የደም አይነቶች፣ የደም አይነቶቹም ኤቢ፣ ኤ፣ ቢ እና ኦ ናቸው።

የደም ግንቦ ደማም፣ ቆንጆ፣ ውብ (ሴት)።

የደም ጋን ስ በሽንጥና በዳሌ መገጣጠሚያ አካባቢ ያለ የሰውነት ክፍል።

ደመኛ (ደበኛ) ቅ ጠላት፣ ባላጋራ።

ደማም ቅ የደስ ደስ ያለው፣ ውብ (ሰው)።

ተዳማ ግ ደም ተፋሰሰ።

አዳማ ግ ደም አፋሰሰ።

ደማሚት (ድማሚት) ስ ተራራ ለመፈንቀል፣ የማእድን ጉድጓድ ለመቆፈር፣... የሚያገለግል ሃይለኛ ፈንጂ።

ደማም "ደማ" ስር ተመ.

ደማቅ "ደመቀ" ስር ተመ.

ደም "ደማ" ስር ተመ.

ደምበኛ "ደነበ" ስር **"ደንበኛ"** ን ተመ.

ደምበጃን(ደንበጃን) ስ የተለያየ መጠን ያለውና ብዙ ፈሳሽ ሊይዝ የሚችል በጣም ትልቅ የሆነ ጠርሙስ።

ደምባራ "ደነበረ" ስር **"ደንባራ"**ን ተመ.

ደምብ "ደነባ" ስር **"ደንብ"** ን ተመ.

ደሞዝ "ደመወዝ" ን ተመ.

ደረመሰ ግ ጠረመሰ፣ ናደ፣ አፈረሰ።

ድርምስ አለ ግ ተደረመሰ።

ተደረመሰ ተጠረመሰ፣ ተናደ፣ ፈረሰ።

ደረመን ስ 1. እከክ፣ ፎከት። 2. የቆምጥና በሽታ።

ደረመናም ቅ 1. (ስድብ) እከካም፣ ፎከታም። 2. የቆምጥና በሽታ ያለበት።

ደረሰ[1] ግ 1. ቀረበ፣ ተጠጋ። 2. መጣ፣ ከች አለ። *በጧት ደረሰ።* 3. ሄደ። *ሃኪም ቤት ደርሶ መጣ።* 4. ገባ። *መንገደኛው በሶስት ሰአት ደሴ ደረሰ።* 5. በቃ። *ልጁ ለወግ ደረሰ።* 6. አደገ፣ ጎለመሰ። *ቤቱን የሚጠብቅ የደረሰ ልጅ አለን።* 7. ሆነ፣ ተፈፀመ። *ንግርቱ ደረሰ።* 8. ዝግጁ ሆነ ለመብላት፣ ለመታወጅ፣ ለመጠጣት፣ ለመሰብሰብ፣...።

ደረሰለት 1. መጣለት፣ ተገኘለት፣...። 2. አለቀለት፣ ተጠናቀቀለት (ስራው)።

ደረሰበት 1. አገኘው፣ አጋጠመው። *መኪና ደረሰበት።* 2. ተተናኘለው ነገር ፈለገው። 3. ተጠጋው፣ ቀረበው።

ደረሰባት በግብረ ስጋ ተገናኛት።

ደረሰው አገኘ፣ ተረከበ፣ ወሰደ። *ሎተሪ ደረሰው።*

አያድርስ አይምጣብኝ፣ አይግጠም (ክፉን ነገር)።

መድረሻ ስ 1. መግቢያ፣ መጠጊያ። 2. አንድ ነገር ከአንድ ቦታ ተነስቶ ሂደቱን የሚያቆምበት፣

የሚያርፍበት ቦታ።

መድረሻ ቢስ መጠጊያ የሌለው።

ደረሰኝ ስ አንድ ግለሰብ ወይም ድርጅት አንድን እቃ ወይም ገንዘብ ከአንድ ድርጅት ወይም ግለሰብ መረከቡን የሚያረጋግጥበትና ለአስረካቢው የሚሰጠው የፅሁፍ ማስረጃ።

ደራሽ ውሃ ስ ድንገተኛ የውሃ ሙላት።

ደርሶ ያለምክንያት ዝም ብሎ። *ደርሶ መታኝ*፤

ደርሶ መልስ1.ሙሉ ጉዞ። 2.ከሄዱበት ቦታ ሳይሰነብቱ ፈጥኖ መመለስ

ደርሶ መልስ ቲኬት ስ ወደ አንድ ቦታ ለመሄጃና ለመመለሻ የሚያገለግል የመጓጓዣ ቲኬት።

-ድረስ መዋ የቦታን፤ የጊዜንና የሃሳብን የተወሰነ መድረሻ፤ ልክ ለመግለፅ የሚያገለግል መስተዋድዳዊ ምእላድ። *ከአዲስ አበባ ደሴ ድረስ/ማታ ድረስ/ እስከዚህ ድረስ አትጨነቅ*።

ድራሽ ቅ 1. አድራሻ፤ የደረሰበት፤ የሄደበት። *ሰውየው ድራሹ ጠፋ*። 2. ድምጥማጥ፤ ማንነት። *ድራሽህ ይጥፋ!*

ድራሹ ጠፋ ያለበት፤ የሚገኝበት የማይታወቅ ሆነ፤ ደብዛው የለም፤ ያለበት አልታወቀም።

ድርስ ስ 1.ለመውለድ የተቃረበች ሴት። 2. ያሬዳዊ የዜማ ምልክት።

ድርሱን ቁርጡን፤ የመጨረሻውን (ለዋጋ)። *ድርሱን ንገረኝ*።

ድርስ እርጉዝ ቅ ለመውለድ ጊዜዋ የደረሰ።

ድርስ ጥርስ ስ የመንቀያው ጊዜ በመድረሱ ሊነቀል የተቃረበ ጥርስ።

ድርሻ ስ እድል፤ ፋንታ፤ እጣ። *ድርሻውን ወሰደ*።

ተደረሰ ግ 1.ተቀረበ፤ መጠጋት ተቻለ። *እዚያ መቼ ተደረሰና ነው?* 2. ሆነ፤ ተደረገ። ስምምነት ላይ ተደረሰ። 3. ተገባ፤ መገኘት ተቻለ። *ልክ በሁለት ሰዓት ከተባለው ቦታ ተደረሰ*። 4. ተበቃ፤ *ለዚህም ተደረሰ እንዴ?*

ተዳረሰ ግ 1. ለሁሉም በቃ። ወረቀቱ ለሁሉም ተዳረሰ። 2. ተግባደደ፤ ቀረበ፤ ተጠጋ። *ጊዜው ተዳርሷል*። 3. ተሰራጨ፤ ተናኘ። *ወሬው በአንዴ ተዳረሰ*። 4. ተነካካ፤ ተገናኘ፤ ተጣላ። *በምን ተዳረሱ?* 5. ሊስማሙ ተቃረቡ(በዋጋ)።

መዳረሻ ስ 1. መቃረቢያ፤ መድረሻ። 2. መቆያ (ምግብ)።

አደረሰ ግ 1. አቀረበ፤ አስጠጋ ። 2. አመጣ፤ *ሰውዬው እዚህ አድርሶኝ ተመለሰ*። 3. ወሰደ፤ *ቤት በመኪና አደረሰኝ*። 4. አበቃ፤ *በሽታው ለሞት አደረሰው*። 5. ፈፀመ፤ አጠናቀቀ፤ አገባደደ። *የልቡን አደረሰ*። 6. አስከተለ። *ጎርፉ ከፍተኛ ጉዳት አደረሰ*። 7. ሰውነቱ ሞላ፤ አደገ፤ ጎለመሰ። *አካሉ መጠን አደረሰ*። 8. ለአካለ መጠን፤ ለሙሉ ሰውነት አበቃ። *ወንድ ልጅ አደረሰ*።

አድርሰናል ቀደም ብሎ ለመጣ ለማኝ ወይም ለጨፋሪ ሰጥተናልና አትቁም፤ የምንሰጥህ የለንም ለማለት ከበር ለቆመ ለማኝ ወይም ለጨፋሪ የሚነገር ቃል።

አድራሻ ስ 1. አንድ ሰው ወይም አንድ ነገር በጊዜያዊነት ወይም በቋሚነት የሚገኝበት፤ የሚኖርበት የተወሰነ ቦታ። 2. አንድ ደብዳቤ ወይም እቃ የትና ለማን መሰጠት እንዳለበት የሚያመለክት፤ በደብዳቤው ወይም በእቃው ላይ የሚሰፍር የፅሁፍ መግለጫ።

አድራሻውን አጠፋ የሚኖርበት፤ የሚገኝበት ቦታ እንዳይታወቅ አደረገ።

አደራረሰ ግ አነካካ፤ አጣላ። *ምን አደራረሳቸው*።

አዳረሰ ግ 1. ለሁሉም በሰፊው ሰጠ፤ ናኘ። 2. ሁሉም ዘንድ እንዲደርስ አደረገ (ወሬ)። 3.ለሁሉም በማይበቃቃት ሰጠ። 4. ለሁሉም ደረሰ፤ በቃ። 5. አገባደደ፤ ለፍፃሜ አቃረበ። 6.አነካካ፤ አጣላ።

አዳራሽ ስ በአንድ ጊዜ ብዙ ሰው ሊይዝ የሚችል ሰፊ የሆነ ቤት ወይም የቤት አንድ ክፍል። 2 ሰፊ።

ደረሰ^{2} ግ ድርሰት አዘጋጀ፤ ፃፈ።

ደራሲ ስ ድርሰት አዘጋጅ፤ ፀሃፊ።

ድርሰት ስ 1. በስድ ንባብ፤ በግጥም፤ በቅኔ፤... መልክ የሚዘጋጅ ስነፅሁፍ። 2. (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) መፅሃፍ ቅዱስን ሳይጨምር በድርሳን፤ በገድል፤ በታምር፤... መልክ የተዘጋጀ የቤተክርስቲያን መፅሃፍ።

ድርሳን(ብ.ቁ.**ድርሳናት**) ስ ስለመላእክት፤ ስለቅዱሳን፤... የተደረሰ መንፈሳዊ መፅሃፍ። *ድርሳነ ሚካኤል*።

አደራረስ ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) በታላቅ በአል ጊዜ ብቻ የሚዘመር ያሬዳዊ የዜማ ድርሰትና ስርአተ ማህሌት።

ደረሰኝ ¨**ደረሰ**^{1}ግ ስር ተመ.

ደረቀ ግ 1 እርጥበት አጣ፤ ከሸለለ። 2 (ዘይ.) ሃሳበ ግትር ሆነ።

ደረቅ ስ 1 እርጥበት፤ ልምላሜ የሌለው። 2 ዘይ.፤ ክፉ፤ ለዛቢስ፤ እፍረተቢስ።

በደረቁ ተው.ግ. ያለምንም ማዋዣ (እህል ውሃ)። *በደረቁ ያደከመኛል* ።

በደረቁ ላጨ አታለለ፤ ሸነገለ።

በደረቅ አፉ ምንም ሳይበላ፤ ሳይቀምስ።

ደረቅ ሌሊት ስ ውድቅት።

ደረቅ ምች ስ ሃይለኛ ምች፣ ከሆድ ሙቀት የተነሳ የሚመጣ ህመም።

ደረቅ ሳል ስ አክታ የሌለው ሳል።

ደረቅ ስንቅ ስ እንደ ኮቸሮ፣ በሶ፣ ቋንጣ ያለ ለብዙ ጊዜ ሳይበላሽ የሚቆይ ምግብ።

ደረቅ ትንቢት ስ መልእክቱ ስውርነት የሌለው፣ ግልፅ የሆነ ትንቢት ወይም ንግር።

ደረቅ እርሳስ ስ ቀለምነት የሌለውና (ኮፒ እርሳስ ያልሆነ) ለመፃፊያ የሚያገለግል እርሳስ።

ደረቅ እንጀራ ስ ወጥ የሌለው እንጀራ።

ደረቅ ወንዝ ስ ውሃ የሌለው ወንዝ።

ደረቅ ወዝ ስ ፎረፎር።

ደረቅ ጉንፋን ስ አክታ የሌለው ጉንፋን።

ደረቅ ግንባር አድለቢስ።

ደረቅ ጠጅ ስ የበሰለ ወይም የቆየ ጠጅ ።

ደረቅ ጣቢያ ስ ለተሳፋሪ ምንም የሚበላ የሚጠጣ የሌለበት የባቡር ጣቢያ።

ደረቅ ጦር ስ የጦር መሳሪያ ያልያዘ ዘማች።

ደረቅ ሽንት ስ ፈሳሽ ነክ ያልሆነ የሽንት አይነት ።

ደረቆት ስ ገብስ ወይም በቆሎ ተቆልቶ ወይም በውሃ በደምብ ርሶ ከተቆላ በኋላ ተፈጭቶ የሚዘጋጅ የጠላ እህል።

ደራቂቻ ቅ 1. ክሲታ፣ ጠማጋ። 2.እርጥበት፣ ልምላሜ የሌለው።

ደራቃ ዝ.ከ.

ድርቅ ስ ዝናም የጠፋበት ወቅት፣ ጊዜ።

ድርቅ መታው ዝናብ አጣ፣ በጋ ሆነ።

ድርቅ ገብቷል በዝናብ መታጣት ምክንያት ረሃብ፣ ችግር ገብቷል።

ድርቄ ስ ጌጥ ያልተሰራለት ወይም በዘበር አረብ ያልተሸለመ ሰገባ፣ አፎት።

ድርቀት ስ 1. እርጥበት አልባነት። 2. የሆድ ወይም የአንጀት ልስላሴ ማጣት የሚያስከትለው ህመም። 3 (ዘይ.) ከንቱ መፏፏት፣ ውጤት ለሌለው ነገር መለፍለፍ።

ድርቅና ስ ለዛቢስነት፣ ችክነት፣ አይን አውጣነት።

ድርቆሽ ስ 1.ታጭዶ የደረቀ ሳር። 2. ሆን ተብሎ እንዲደርቅ የተደረገ እንጀራ (የተወቀጠ ወይም ያልተወቀጠ)።

ድርቅ አለ ግ በጣም ደረቀ።

ተጻረቀ ግ 1. (ዘይ.) ተነታረከ፣ ተፏፏሀ፣ ተለፋለፈ፣ ተጨቃጨቀ። 2. ተሰላቸ፣ ታከተ (በነገር፣ በጭቅጭቅ)።

አደረቀ ግ (ዘይ.) አሰለቸ፣ አታከተ (በነገር፣ በጭቅጭቅ)።

አድርቅ (ልብ አድርቅ) ቅ 1. ነዝናዥ፣ ጨቅጫቂ። 2. በተደጋጋሚ በንግሩም፣ በመከሩም ለሰው የሚያሳይ፣ የሚነገረውን ተግባራዊ የማያደርግ፣ ልብ አውልቅ።

ደረበ ግ 1. አንዱን በሌላው ላይ አደረገ፣ ጨመረ፣ ጫነ፣ አነባበረ። 2. በለበሰው ልብስ ላይ ሌላ ልብስ ጨምሮ ለበሰ። 3. ጨመረ፣ ደአከለ። *ይህ ቃል ሌላ ፍች ደርቦ ይዟል።*

መደረቢያ (ድራብ) ቅ እንደኩታ፣ ቡሉኮ ወዘተ. ያለና ከልብስ በላይ የሚለበስ ልብስ።

ደርብ ስ በድሮ ጊዜ የሚሰራ ባለአንድ ፎቅ ቤት።

ድርብ ቅ 1. እጥፍ ። 2. የተደረበ። 3. ስ ስራ ጥበብ ያለውና የማእረግ ልብስ የሆነ ኩታ (ጥንድ ድርብም ይባላል)። 4. የሸማ ጥበብ አሰራር አይነት።

ድርብ ሰረዝ ስ ከስርአተ ምልክቶች አንዱ ምልክቱም (፤) ነው።

ድርብ ቃል ስ ጥምር ቃል።

ድርብ ታቦት ስ በአንድ ቤተክርስቲያን ውስጥ በደባልነት የሚገኝ ሌላ ታቦት፣ ደባል ታቦትም ይባላል።

ድርብ ትርጓሜ ስ አንድምታ።

ድርብ ዜማ ስ ንባቡ አንድ አይነት ሆኖ ዜማ ወይም ምልክቱ ከአንድ በላይ የሆነ።

ድርብ ጃኖ ስ የጥለቱ ጻርና ጻር በድርብ ጥበብ አሰራር የተከበበ ጃኖ።

ድርብ ጥርስ ስ በጥርስ ላይ ተደርቦ የሚወጣ ጥርስ።

ተደረበ ግ 1. በእግር ኳስ ጨዋታ ላይ የተመታችን ኳስ አቅጣጫዋን እንድትስት አደረገ። 2. አበረ፣ አገዘ። *ተደርቦ መታው።*

ተደራቢ ቅ ተጨማሪ።

ተደራረበ ግ 1. አንዱ በሌላው ላይ ሆነ፣ ተነባበረ። 2. ተጨማመረ፣ በላይ በላዩ ሆነ።

ተደራራቢ ቅ ተደጋጋሚ፣ አንዱ በሌላው ላይ የመጣ፣ የሆነ፣ የተደረገ።

አደራረበ ግ አንዱን በሌላው ላይ አደረገ፣ ጫነ፣ አነባበረ።

***ደረበበ**

ደርባባ ቅ 1. ሰውነቱ ወፈር፣ ደልደል ያለ (ሰው)። 2. ረጋ ያለ፣ ጭምት፣ ዝምተኛ።

ድርበብ ስ የመስፈሪያውን እቃ (ቁና፣...) እስከ አፉ ድረስ ብቻ የሚሞላ የጥሬ ጥሬ ወይም የደረቅ ነገር የአሰፋፈር አይነት፣ ተቆልሎ ያልተሰፈረ።

በድርበቡ በልኩ፣ በመጠኑ፣ እንደነገሩ።

ፍትራትን በድርበቡ ነው።

ተንደረበበ ግ 1. እስከመስፈሪያው እቃ አፍ ድረስ ብቻ ሞላ፤ ተሰፈረ። 2. ጨመተ፤ ዝም አለ።

አንደረበበ ግ እስከመስፈሪያው እቃ አፍ ድረስ ብቻ አስተካክሎ ሰፈረ።

ደረባ ስ በግሬያ መልክ የተዘጋጀ የጎተራ ክዳን።

ደረቧ ግ ናደ፤ አፈለሰ፤ አፈረሰ።

ደረተ ግ 1. አንድን ጨርቅ በሌላው ላይ እየደረበ መሳልቦ ሰፋ። 2. ደራረበ።

ድሪቶ ስ 1. ተደራርቦ ብዙ ቦታ ላይ የተሰፋ አሮጌ ጨርቅ። 2. የተቀጻጸደና ቡትቶ የሆነ ልብስ። 3. (ዘይ.) የተደጋገመ (ሃሳብ)። 4. (ስድብ) ፊቱ ላይ ጠቃጠቆ (ጠባሳ) ያበዛበት (ሰው)።

ድሪቷም ቅ 1.(ስድብ) ድሪቶ ለባሽ። 2. ደሃ።

ድርት ቅ ተደራርቦ የተሰፋ፤ ቡትቶ።

ደረት ስ 1. በሰተፊት በኩል ከአንገት በታች ከሆድ በላይ ያለ የሰውነት ክፍል። 2. ያሬዳዊ የዜማ ምልክትሐ።

ደረቱን ገልብጦ ያለፍርሃት፤ በትእቢት።

ደረቷን ደቃች ደረቷን መታች (በልቅሶ ጊዜ)።

ደረቷን ጣለች በሃዘን ምክንያት ደረቷን አራቁታ ሃዘኗን ገለፀች።

*ደረከከ

ደረከከ (ደርኳካ) ቅ አጭር ወፍራም።

ድርክክ አለ ግ 1. በጣም በሰለ (ፍሬ)። 2. ፋመ፤ ፍም ወረደው (እሳት)። 3. አጭርና ወፍራም ሆነ።

ተንደረከከ ግ 1. አጭርና ወፍራም ሆነ።2. በጣም በሰለ፤ ጎመራ (ፍሬ)። 3. በጣም ፋመ፤ ፍሙ መረተ (እሳት)። 4. ቀስ ብሎ በአጭር ተራመደ (አጭር ወፍራም ሰው)።

አንደረከከ ግ 1. አጭርና ወፍራም አደረገ። 2. አበሰለ (ፍሬን) ። 3. ፍም እንዲሠማው፤ እንዲወርደው አደረገ።

ደረዘ ግ 1. ሰገመ፤ ከፈፈ (ስፌድን፤ መሶብን፥...)። 2. እንደ በተሰፋው የስፌት መስመር አስጠግቶ እንደ ገና ሰፋ፤ ደርዝ አበጀ።

ደርዝ ስ 1. ክፈፍ (የስፌድ፤ የመሶብ፥...)። 2.ስፌት ተደጋግሞ የሄደበት የልብስ ዳርቻ።

ደርዝ ያለው ንግግር ሙሉ፥ መልክ፤ ጭብጥ፤... ያለው ንግግር።

ደርዘኛ ቅ 1. አነጋገር አዋቂ። 2. እምነት ጠባቂ።

ደረደረ ግ 1 በተራ፥ በረድፍ አደረገ፤ ሰደረ፥ ኮለኮለ፤ አሰለፈ። 2. አንባበረ፤ ቆለለ፤ ከመረ። 3.ሃሳብን አንድ ባንድ ገለፀ፤ አሰማ። *ግጥም ደረደረ/ሰበብ ደረደረ።* 4.መታ፤ ገረፈ፤ *ነዘረ(በገናን)* ።

መደርደሪያ ስ ከእንጨት፤ ከብረት፥... በተለያየ መጠንና ቅርፅ የሚሰራና ልዩ ልዩ እቃዎችን በረድፍ ለማስቀመጥ የሚያገለግል እቃ። *መፃሕፍት መደርደሪያ/እቃ መደርደሪያ፡*

ድርድር ስ በረድፍ የተቀመጠ እቃ።

ድርድር ስ አንድን ነገር ወይም ሁኔታ አስመልክቶ ስምምነት ላይ ለመድረስ የሚደረግ፤ ውይይት።

ተደረደረ ግ በረድፍ፤ በተራ ተሰደረ፥ ተኮለኮለ።

ተደራደረ ግ ተዋዋለ፤ ተስማማ፤ ተነጋገረ (እንደዚህ ይሁን ወይም አይሁንም፥ እንደዚያ ነው ወይም አይደለም እየተባባለ በመከራከር)።

ተደራዳሪ ቅ 1. ውል ተዋዋይ። 2. አንድን ጉዳይ አስመልክቶ ከሌላ ወገን ጋር እንዲነጋገር፤ እንዲከራከርና ስምምነት እንዲያደርግ ውክልና የተሰጠው (ሰው)።

አደራደረ ግ አዋዋለ፤ አስማማ።

አደራዳሪ ስ አዋዋይ፤ አስማሚ።

*ደረደረ

ተንደረደረ ግ 1. ከከፍተኛ ወደ ዝቅተኛ ቦታ ሮጠ። 2. ተፈተለከ፤ በሃይል ሮጠ።

መንደርደሪያ ስ 1. ለመሮጥ አመቺ የሆነና ተዳፋትነት ያለው ቦታ። 2. መነሻ፥ መጀመሪያ (የሃሳብ)። 3. ለማረፍ ወይም ለመነሳት የሚያገለግል ማኮብኮቢያ (ለአውሮፕላን)።

አንደረደረ ግ አሮጠ።

ደረጀ ግ 1. ጠና፤ ጠነከረ። 2. ተደላደለ፤ ሀብት ያዘ፤ ንብረት አበጀ።

ደረጃ ስ 1. ለመውጫና ለመውረጃ የሚያገለግል እርከን (በአብዛኛው ለፎቅ ቤቶችና ከፍታ ላይ ለሚገኙ ቦታዎች)። 2. ማእረግ (የትምህርት፥ የሹመት፤...)። 3. ቅደም ተከተል። *ጉዳዩን ደረጃ በደረጃ እናየዋለን*፡ 4. ጥራት። *ለውጭ ገበያ የሚቀርበው ቡና ደረጃው ከፍ ያለ ነው*፡ 5. አቅም፤ ችሎታ። *የሶስተኛው ዓለም ህዝብ የኑሮ ደረጃ ዝቅተኛ ነው*፡ 6. ክብር፥ ልክ። ደረጃህን ጠብቅ።



ደረጃ 1ኛ ፍቺ

ድርጅት ስ 1. የተወሰነ የስራ አይነት የሚካሄድበት ወይም የሚከናወንበት የስራ ተቋም (ፋብሪካ፥ ሆቴል፥...)። 2. ዝግጅት። 3. የተወሰነ አላማን ለማራመድ ሰዎች በአባልነት የሚሰባሰቡበት ማእከል፥ ማህበር፥...።

ተደረጃጀ ግ ተዘጋጀ፥ ተሰነዳዳ።

ተደራጀ ግ 1. ተጠናከረ፥ ተደላደለ። 2. ተዘጋጀ፥ ተሰናዳ። 3. ተሰባሰበ፥ አባል ሆነ (በፖለቲካ ድርጅት፥ በሙያ ማህበራት፥ ...)።

አደረጀ ግ አጠና፥ አጠነከረ፥ አጎለበተ።

አደራጀ ግ 1. አዘጋጀ። 2. ሰዎች በፖለቲካ ድርጅት፥ በማህበር፥... እንዲሰባሰቡ አደረገ።

***ደረገ**

ድርጊት ስ ተግባር፥ ስራ፥ ክንውን።

ተደረገ ግ 1. ተከናወነ። 2. ተፈጸመ፥ ተሰራ። 3. ሆነ።

ተደራጊ ቅ (ሰዋ.) የድርጊት ተቀባይነትን የሚያመለክት (ግስ፥ ቅፅል)።

ተደራራጊ ቅ (ሰዋ.) እርስበርስ አንዱ በሌላው ላይ ድርጊት መፈፀሙን የሚያመለክት (ግስ፥ ቅፅል)።

ተደራጊ ዝ.ከ.

አደረገ ግ 1. አከናወነ፥ ፈፀመ፥ ሰራ። 2.አኖረ፥ አስቀመጠ። *ደብተሩን ጠረጴዛ ላይ አደረገ*። 3. ለበሰ፥ አጠለቀ፥... (ልብስን፥ ሰአትን ጫማን፥...)።

ቁርስ አደረገ በላ፥ ተመገበ፥...።

አድራጊ ቅ (ሰዋ.) 1. ድርጊት ፈፃሚነትን የሚያመለክት (ግስ .ቅፅል)። 2. ፈፃሚ፥ አከናዋኝ።

አድራጊ ፈጣሪ ሁሉን ነገር የሚያደርግ፥ ምንም የማይሳነው፥ አዛዥ።

አደረገ ግ 1. በድርጊት፥ በስራ አገዘ፥ ረዳ። 2. አገናኘ (በጋራ እንዲሰሩ)።

አደራራጊ (ሰዋ.) 1. የድርጊት አጋዥነትን የሚያመለክት (ግስ፥ ቅፅል)። 2. ሁለት ነገሮች እርስ በርስ አንዱ በሌላው ላይ አንድ ድርጊት እንዲፈፅምበት ማስደረጉን የሚያመለክት (ግስ፥ ቅፅል)።

አዳረገ ግ አደራረገ።

አዳራጊ ቅ አደራራጊ።

አሰደረገ ግ 1. አሰራ፥ አሰበጀ። 2. አስፈፀመ (አንድን ድርጊት) ።

አስደራጊ ቅ (ሰዋ.) ለአንድ ድርጊት መፈፀም ምክንያት መሆኑን የሚያመለክት (ግስ፥ ቅፅል)።

ደረገመ ግ 1. አጠፋ፥ እልም አደረገ (መብራትን፥ አይንን፥...)። 2. በሃይል ዘጋ (መዝጊያን)። 3. **መታ** (በጥፊ)። 4. (ዘይ.) ከሚፈለገው በላይ ጨመረ። *ወጡ ውስጥ ጨው ደረገመችበት*።

ተደረገመ ግ 1. ጠፋ፥ እልም አለ። 2. በሃይል ተዘጋ።

***ደረፏጨ**

ደርፏጫ(ድርፏጭ) ቅ አጭርና ጎነ ሰፊ የሆነ።

ድርፏጭ አለ ግ ደርፏጫ ሆነ።

ድርፏጭ አደረገ ግ ደርፏጫ አደረገ ።

ደራ^{1} ግ ዘበጠ፥ ተሰመጠ።

ድራት ስ ዝብጠት፥ ለማማነት።

ደራ^{2} ግ 1. ጋለ፥ ሰማ(ምጣድ)። 2. ሞቀ፥ ደመቀ (ገበያ፥ ጨዋታ)።

***ደራ**^{1}

ደራች ግ የግብረ ስጋ ግንኙነት ፈለገች (ለእንስሳ)።

ድሪያ(ድሪ) ስ ለፍቅር የሚፈላለጉ ሴትና ወንድ የሚያደርጉት ልፊያ፥ ጨዋታ።

ተዳራ ግ ተላፋ፥ ተቃበጠ።

***ደራ**^{2}

ድር ስ ዘሃ፥ ቀጭንና ጠንካራ የሆነ ፈትል ።

ድርና ማግ ሆኑ የግብረ ስጋ ግንኙነት አደረጉ፥ መርፌና ክር ሆኑ።

ተደራ ግ ተተራተረ፥ ተዘረጋ(ድር፥...)።

አደራ ግ ተረተረ፥ ዘረጋ (ድርን፥...)

ደራሲ "ደርሰ^{2}**"** ስር ተመ.

ደራሽ "ደረሰ^{1}**"** ስር ተመ.

ደራቁቻ "ደረቀ" ስር ተመ.

ደራች "*ደራ^{1}**"** ስር ተመ.

ደራጎን ስ በጥንታዊ ታሪኮች ውስጥ የሚጠቀስ (አብዛኛውን ጊዜ ክንፍ ያለው እሳት የሚተፋ፥ አጫጭር እግሮች ያሉት) ዘንዶ መሰል አውሬ።

ደሬ ስ በቆላ የሚገኝ፥ እንጨቱ ጠንካራ የሆነ የዛፍ አይነት ።

ደራጎን

ደርበት ስ ሁለት እንስራ ያህል ውሃ ሊይዝ የሚችል የሸክላ እቃ።

ደርባባ "*ደረበበ" ስር ተመ.

ደርብ "ደረበ" ስር ተመ.

ደርካካ “*ደረከከ” ስር “ደረከከ” ን ተመ.

ደርዘን ስ ብዛቱ 12 የሆነ ተመሳሳይ እቃ።

ደርዝ "ደረዘ" ስር ተመ.

ደርግ ስ ኮሚቴ።

ደርፋጫ "ደረፈጨ" ስር ተመ.

ደሰመ ግ ገጨ፤ ለተመ፡ መታ።

ደሰሰ ግ ዘመመ፡ ዘንበል ሆነ።

ደሳሳ ቅ ያዘመመ፤ ያጎነበሰ (ጎጆ)።

ተንዳሰሰ ግ ደሳሳ ሆነ።

*ደበበ

ተንዳሰሰ ግ አዘገመ፡ ተንቀረሰሰ።

እንዳሰሰ ግ አንቀረሰሰ፤ በዝግታ አስኬደ።

ደሰቀ ግ 1. መታ፡ ደቃ (በክርን፡ በጡጫ)። 2. ተጫጫነ፤ ደበተ (እንቅልፍ)።

ደሰቅ ስ የሚደብት፡ የሚጫጫን እንቅልፍ።

ደሰቃም ቅ የሚያስፈራ፤ የሚቀፍ፤ የሚደብት ቦታ።

*ደሰተ

ደስታ ስ ፍስሃ፤ ሃሴት፡ ፈንጠዝያ የሞላበት ወይም ሃዘን፡ ትካዜ፡... የሌለበት ሁኔታ።

በደስታ ሰከረ በጣም ተደሰተ።

በደስታ ዋኘ በጣም ተደሰተ።

ደስተኛ ቅ 1. በአንድ ነገር ወይም ድርጊት የተደሰተ። 2 በአኗኗሩ፤ በህይወቱ ርካታ ያገኘ፡ ብዙ ጊዜ የሃዘን ስሜት የማይታይበት።

ደስ አለ ግ ቆንጆ፡ ማራኪ፤ አስደሳች፡... ሆነ።

ደስ አለው ግ ተደሰተ።

ደስ የሚል ቅ ቆንጆ፤ ማራኪ፡ አስደሳች።

ደስ አሰኘ ግ አስደሰተ።

ደስ ደስ አለው ግ ተደሰተ።

የደስ ደስ የተገኘውን ደስታ ምክንያት በማድረግ የሚደረግ ግብዣ ወይም ስጦታ።

የደስደስ ያለው 1. ቆንጆ፡ ውብ፡ ማራኪ የሆነ። 2. ደስታ የተሰማው፡ በደስታ የተሞላ።

ተደሰተ ግ ደስታ ተሰማው፡ ፈነደቀ።

ተደሳች ቅ ህይወት የፈካችበት፤ ችግር፤ ጭንቀት፤ ብስጭት፤ ሃዘን፡ ትካዜ፡... የማይታይበት።

አስደሰተ ግ ደስታ እንዲሰማው፡ እንዲያገኝ አደረገ።

አስደሳች ቅ ውብ፡ ማራኪ፡ ደስታ የሚሰጥ።

ደሳሳ "ደሰሰ¹" ስር ተመ.

ደሴት ስ በውሃ (በባህር) የተከበበ መሬት ።

ደስቃም "ደሰቀ" ስር ተመ.

ደሰቅ ገ.ከ.

ደስተኛ “*ደሰተ” ስር ተመ.

ደስታ¹ ገ.ከ.

ደስታ² ስ 1. የከብት በሽታ አይነት። 2. በቶሎ የምትለቅ የኩፍኝ በሽታ አይነት።

*ደሸደሸ

አደሸደሸ ግ አዘጠዘጠ፤ አደዘደዘ፡ አውደለደለ።

አደሽዳሽ ቅ(ስድብ) አዘጥዛጭ፡ አውደልዳይ።

ደቀለ ግ ዲቃላ ወለደ።

ዲቃላ ስ 1. ከጋብቻ ውጭ የተወለደ ልጅ። 2. የተለያዩ ዘር፡ ቀለም ካላቸው ሰዎች የተወለደ ልጅ (ለምሳሌ ጥቁር ከነጭ) 3. መሊቃ፡ ክልስ። 4. (ዘይ.) የተለየ፡ የማይገጥም።

ተደቀለ ግ ከጋብቻ ውጪ ተወለደ።

ተዳቀለ ግ 1. ተዛመደ (በመውለድ)። 2. ከሁለት የተለያዩ ዘሮች ተፈጠረ፡ ተወለደ (ለአዝርእት፡ ለእፀዋት፡ ለእንስሳት፡...) ።

አዳቀለ ግ ሁለት የተለያዩ ዘሮችን በማገናኘት ለየት ያለ ዘር እንዲፈጠር አደረገ።

ደቀመዝሙር(ብ.ቁ.**ደቀመዛሙርት**) ስ 1. (ቤ.ክ.) ተማሪ። 2. የአላማ ተከታይ።

ደቀቀ ግ 1. ለዘበ፡ ላመ፡ 2. ተሰበረ፡ ነከተ፤ መሸከ። 3. ትናንሽ ሆነ፡ ረቀቀ (ፅሁፍ፡...)። 4. ጫጨ፤ ቆረቆዘ። 5. (ዘይ.) ደከመ፡ ዛለ። *ሰውነቱ ደቀቀ*።

ደቂቃ ስ የአንድ ሰአት 1/60ኛ የሆነ የጊዜ ክፍልፋይ።

ደቂቅ ቅ 1. በጣም ትንሽ፤ ለአይን ጎልቶ የማይታይ። ስ 2. ልጅ። *ከሊቅ እስከ ደቂቅ* ።

ደቃቃ ቅ 1. በጣም ትናንሽ የሆነ። 2. (ዘይ.) ደካማ፡ አቅመቢስ።

ደቃቅ ቅ 1. ልም፡ ልዝብ፡ የተሰለቀ። 2. በጣም ጥቃቅን የሆነ።

ድቃቂ ቅ ስብርባሪ፡ ንኩትኳች።

ተዳቀቀ ግ ተዳከመ፡ አቅም አጣ።

አደቀቀ ግ 1. ፈጨ፡ አለዘበ፤ አላመ። 2. ሰባበረ፡ አመሸከ። 3. አደከመ፤ አቅም አሳጣ። 4. አቀጫጨ፡ አረቀቀ(ፅሁፍን)።

ደቀነ ግ 1. ከሚወርደው ወይም ከሚፈሰው ነገር ስር መቀበያ የሚሆን እቃ አስጠጋ፡ አስቀመጠ፡ ሰገተ። *ከዝንዟው ስር ባልዲ ደቀነ*። 2. ጀመረ፤ ወጠነ። 3. ደገነ፡ አነጣጠረው አለመ። 4. ጋረጠ።

ድቅን ጅምር፡ ውጥን።

ተደቀነ ግ ተጋረጠ። እፊቱ እየተደቀነ አስቸገረኝ።

ደቀደቀ ግ 1. ጠቀጠቀ፣ ተመተመ። 2. መታ፤ ደበደበ። 3. ቆፈረ።

መደቅደቂያ ስ የጠመንጃን አፈሙዝ (ቧንቧውን) ለመጥረግ የሚያገለግል ቀጭን ብረት።

ድቅድቅ ቅ 1. የተጠቀጠቀ፣ ጥቅጥቅ። 2. አንድ ጊዜ የታረሰ (መሬት)። 3. ቁፍር።

ድቅድቅ ጨለማ ድፍን ያለ፣ ምንም የማይታይበት ጨለማ።

***ደቀደቀ**

ተንደቀደቀ ግ 1. ደቅ፣ ደቅ የሚል ድምፅ ሰጠ፤ ተንበቀበቀ። 2. የፉከራ ድምፅ አሰማ።

እንደቀደቀ ግ 1. ደቅ ደቅ የሚል ድምፅ እንዲሰጥ አደረገ፤ አንበቀበቀ። 2. የፉከራ ድምፅ አሰማ።

ደቂቃ "ደቀቀ" ስር ተመ.

ደቂቅ ዝ.ክ.

ደቃ ግ መታ (በጡጫ፣ በክርን፣...)።

ደቅ አለ ግ ጓ፥ ደቅ የሚል ድምፅ አሰማ።

ደቅ አደረገ ግ ደቃ።

ደቃቃ "ደቀቀ" ስር ተመ.

ደቃቅ ዝ.ክ.

ደቅ ስ ከማባ የሚበልጥ፣ ከዋዲያት የሚያንስ የሸክላ እቃ።

ደቆሰ ግ 1. በመደቆሻ አደቀቀ፣ አላመ። 2. ጨፈለቀ። 3. (ዘይ.) ደበደበ መታ።

መደቆሻ ስ 1.አነስተኛ የድንጋይ ወፍጮ። 2. ለመደቆስ የሚያገለግል ጠፍጣፋ እንጨት።

ድቁስ ስ የበርበሬ ዱቄት።

ተደቆሰ ግ 1 ላመ፣ ደቀቀ። 2 ዛለ፣ ደከመ።

ተዳቆሰ ግ ተማታ፣ ተደባደበ።

ደበለ ግ 1. ጨመረ፣ ደረበ። 2. ቀየጠ፣ ደባለቀ፣ ቀላቀለ። 3. ሸረበ፣ ጠመረ፣ በአንድነት ፈተለ (የተለያዩ ክሮችን፣...)።

ደባል ስ 1.የሌላ ሰው ይዞታ በሆነ ቤት ውስጥ ተደርቦ የሚኖር ሰው። 2. በአንድ ቤተ ክርስቲያን በድርብነት የሚገኝ ታቦት። ቅ 3. ተጨማሪ፣ ተቀፅላ፣ ተደራቢ፣ በፊት ያልነበረ። *ደባል ባህርይ ላወጣ።*

ድብል ስ ወፍራም ሸርብ ገመድ።

ተዳበለ ግ 1. ደባል ሆነ። 2. አንድ ነገር ከሌላ ነገር ጋር ባንድ ላይ እንዲቀመጥ ተደረገ።

አዳበለ ግ 1. ከቤቱ ደባል አስቀመጠ። 2. አንድን ነገር ከሌላ ነገር ጋር ባንድነት አስቀመጠ።

ደበለለ^{1} ግ ጣለ፣ አንከባለለ።

ተንደባለለ ግ ተንከባለለ።

አንደባለለ ግ አንከባለለ።

ደበለለ^{2} ግ አከበደ፣ ትልቅ አ ደረገ (ሸክምን)።

ድብል ቅ ትልቅ ሸክም።

ተደበለለ ግ ትልቅ ሸክም ተሸከመ።

ደበለቀ "ደባለቀ" ን ተመ.

***ደበለበለ (*ደቦለቦለ)**

ድብልብል(ድቡልቡል) ቅ 1. እንደአለሎ፣ እንደኳስ ያለ፣ ክብ፣ እንክብል። 2. መላ አካሉ የወፈረ።

ድብልብል(ድቡልቡል)አለ ግ ተድበለበለ።

ድብልብል(ድቡልቡል) አደረገ ግ አድበለበለ።

ተድበለበለ(ተድቦለቦለ) ግ 1. ድብልብል ሆነ። 2. ወፈረ (መላ አካሉ)።

አድበለበለ(አድቦለቦለ) ግ 1. ድብልብል አደረገ። 2. አወፈረ (መላ አካሉን)።

ደበላ ስ እንደሻሽ፣ መጋረጃ፣... ሆኖ ሊያገለግል የሚችል ስስ የአቡጀዲ አይነት።

ደበላለቀ "ደባለቀ" ስር ተመ.

ደበሎ ስ 1. ከነጠጉሩ ከተለፋ በኋላ በክብ ቅርፅ ተቀጣጥለው የተሰፉ የቆሎ ተማሪዎች የሚለብሱት የበግ ቆዳ። 2. ከነጠጉሩ ከተለፋ በኋላ በሰምድ መልክ ትከሻ ላይ የሚለበስ የበግ ቆዳ።

ደበሎ

ደበረ^{1} ግ ደብር ወይም ገዳም አደረገ፣ የደብርነት ወይም የገዳምነት ማእረግ ሰጠ።

ደብር(ብ.ቁ.አድባራት) ስ 1. በአስተዳደር እርከን፣ በካህናት፣ በመፃህፍት፣ በመምህራንና በሃብት ብዛት አንፃር ማእረጉ ከገጠር ቤተክርስቲያን የላቀና እንደ መወድስ፣ ሰአታት፣ ማህሌት፣ ቅዳሴ፣... የመሳሰሉት መንፈሳዊ ተግባራት በተወሰኑ ጊዜያት ተዘውትረው የሚከናወኑበት ቤተክርስቲያን። 2. ገዳም።

ደብረ በጥብጥ ረባሽ፣ በጥባጭ።

አድባር ስ 1. ብዙውን ጊዜ በቤት የምትጠራ የመናፍስት አይነት፣ ቆሌ። 2. የአካባቢው ቆሌ ወይም መንፈስ የሚኖርበት ነው በሚል እምነት ሰዎች ቅቤ በመቀባት፣ ቡና በማፍላት፣... የሚያከብሩትና አምልኮ የሚያደርጉበት ዛፍ፣ ድንጋይ፣...።

አድባር ነው በሚኖርበት አካባቢ በከበሬታ አይን የሚታይ ታላቅ አዛውንት ነው። *አከሌ*

አድባር ነው።

ደበረ^2 ግ 1. ደረበ፥ አነባበረ፥ ደበለ። 2. ሰደረ፥ ደረደረ፥ በተርታ አስቀመጠ።

ደበረ^3 ግ (የአራዳ አነ.) አሰጠላ፥ ተጫጫነ፥ ቀፈፈ።

ደባሪ ቅ አሰጠሊታ፥ ቀፋፊ።

ድብርት ስ የመቀፈፍ፥ የመክበድ፥ የመጫጫን ሁኔታ።

ድብር አለ ግ ተደበረ ወይም ደበረው።

ተደበረ ግ ቅፍፍ አለው፥ አስጠላው፥ ደስ የሚል ስሜት አጣ።

ደበሰ ቅ ነዘዘ፥ ደበዘዘ፥ ቆሸሸ፥ ቀልሞ ብሎ አልታይ አለ (ጽሑፍ፥ ስእል፥...)።

ድብስብስ(ደበስባሳ) ቅ 1.ቀልሞ ብሎ የማይታይ፥ ጭምንምን፥ የደበዘዘ። 2. በጥራት ያልተሰራ።

ተድበሰበሰ ግ 1.ተሸፋፈነ፥ ተለባበሰ (ነገሩ፥...)። 2. በጥራት፥ በደንብ ሳይሰራ ቀረ።

አድበሰበሰ ግ ሸፋፈነ፥ ለባበሰ (ነገሩን፥...)።

***ደበሰሰ**

ደበሰሰ(ደብሳሳ) ቅ ቆርሳሳ፥ ጎታታ።

ተንደበሰሰ ግ ተንቀረሰሰ፥ ተጎተተ፥ አዘገመ።

አንደበሰሰ ግ አንቀረሰሰ፥ ጎተተ።

ደበስባሳ "**ደበሰ**" ስር "**ድብስብስ**" ን ተመ.

ደበሽ(አዲበሽ) ቅ 1. ፈዛዛ፥ ንቃት የሌለው። 2.ግድየለሽ፥ ሰነፍ ቸልተኛ። 3. ወፍራም (ለህፃን)።

ደበቀ ግ 1. ሰወረ፥ ሸሸገ። 2. እንዳይታወቅ አደረገ።

ደበቅ ቅ ስውር፥ ሰዋራ (ቦታ)።

ደበቅ ጦር ስ ያሸመቀ ጦር።

ደባቃ ቅ ሰዋራ (ለቦታ)።

ድብቅ ቅ ስውር፥ ምስጢር የሆነ።

ድብብቆሽ ስ 1. የተደበቀውን ልጅ ፈልጎ ለማግኘት የሚደረግ የልጆች ጨዋታ ። 2. ነገሩ ለሁሉም ወገን ግልፅ ሆኖ ሳለ አንዱ ሌላውን ለማሞኘት የመሞከር ድርጊት።

ተደበቀ ግ ተሰወረ፥ ተሸሸገ፥ ምስጢር ተደረገ።

ተደባበቀ ግ 1. ተደበቀ። 2. አንዱ ለሌላው ግልፅ የሆነ ሃሳብ ነፈገ።

ደበበ ግ ጠየመ፥ ደበሰ።

ደባባ ቅ ጠይም።

ደበተ^1 ግ 1. ተጫነ፥ ከበደ፥ ገረዘዘ (እንቅልፍ)። 2. አንዱን በሌላው ላይ ጫነ፥ ቆለለ።

ደበተ^2 ግ 1. እንዲርስ እንዲለሰልስ በጭቃ ውስጥ ቀበረ (የእንጨት ልጥን)።2. በአዛባ አጅሉ አቆየ (ገበታን፥ ቆሬን፥...)።

ደበተረ ግ የድብትርናን ትምህርት ተማረ፥ አወቀ።

ደብተራ ስ 1. የዜማ፥ የአቋቋም፥ የቅኔ፥... ምሁር፥ መዘምር። 2. መፅሃፍ ገላጭ፥ ኮከብ ቆጣሪ ።

ድብትርና ስ የደብተራነት ሙያ፥ ትምህርት፥ ስራ ።

ደበነ ግ 1. በጣም ጠበቀ፥ ከረረ። 2. በጣም አጠረ፥ ከረረ። 3. አረረ፥ ተቃጠለ፥ ደረቀ። 4.በጣም ተናደደ።

ድብን አድርጎ ቆነጠጠ አጥብቆ በሃይል ቆነጠጠ።

ድባኖ ቅ በጣም አጭር፥ ከራራ።

ደበኔ ስ ዋኔ፥ ቡላል።

ደበን^1 ቅ ቆሻሻ፥ እድፍ።

ደበን^2 ስ ፀጉር።

ደበን^3 ቅ ሞኝ፥ ነሆለል።

ደበን አንሳ ስ (የማንኳኳስ አነ.) ባለእጅ።

ደበኛ "**ዶማ**" ስር "**ደመኛ**" ን ተመ.

***ደበከበከ**

ድብክብክ ቅ 1.ዝብጥብጥ፥ ድፍርስ፥ አተላ የበዛበት። 2.በጣም ወፍራም (ሰው፥...)።

ድብክብክ አለ ግ ተድበከበከ።

ተድበከበከ ግ 1.ተዝበጠበጠ፥ አልጠራ አለ፥ አተላው ከጥሩው አልለይ አለ።.2. በጣም ወፈረ (ሰው፥...)።

አድበከበከ ግ 1.አዝበጠበጠ፥ አተላ አደረገ። 2. አወፈረ (ሰው፥...)።

ደበዘዘ ግ 1. ብሩህነት፥ ደማቅነት አጣ። 2.ደከመ፥ ፈዘዘ። 3. (ዘይ.) ጎልቶ የማይታይ፥ የማይታወቅ ሆነ፥

ደብዛዛ ቅ 1. ብሩህነት፥ ደማቅነት የሌለው (ቀለም)። 2. ደካማ፥ ፈዛዛ (ብርሃን)።

***ደበዘዘ**

ደበዘገ ቅ ቀርፋፋ፥ ጎታታ።

ተንደበዘዘ ግ ቀስ አለ፥ ተንቀረፈፈ።

አንደበዘዘ ግ አንቀረፈፈ፥ ቀስ አደረገ።

***ደበየ**^{1}

ድባያት(ደበያት) ስ በቀል።

ደባይ ቅ 1. ወራሪ፥ ዘራፊ። 2. ድንገተኛ አደጋ።

አደባየ ግ 1. አሸነፈ፡ ረታ። 2. ጣለ፡ ረገጠ፡ አፈረ አስጋጠ።

***ደበየ**²

ደባ ስ ተንኮል፥ ሴራ።

አደባ ግ አደፈጠ፡ አሸመቀ (ለመምታት ስራ)።

ደበያት¹ (**ደባያት**፥ **ደብያት**) ስ ወንፈል፡ ደቦ፡ ጅጌ።

ደበያት² "***ደበየ**²" ስር "**ደባያት**" ን ተመ.

ደበደበ¹ ግ 1. መታ፡ ቀጠቀጠ። 2. አበሰበሰ፡ አራሰ፡ መታ (ዝናብ) ።

ደብዳቢ ቅ መቺ።

ድብደባ ስ የመምታት ወይም የመመታት ድርጊት።

ድብድብ ስ 1. እርስ በርስ መመታታት፡ የእክል ግጭት፡ መፈናከት። 2. ልፊያ ትግል።

ተደበደበ ግ 1. ተመታ፡ ተቀጠቀጠ። 2. በሰበሰ፡ ራሰ (በዝናብ)።

ተደባደበ ግ 1. መታ። 2. ተማታ፡ ተቀጣቀጠ፡ ተናረተ (እርስ በርስ)። 3. ተላፋ።

ተደባዳቢ ቅ ዱለኛ፥ ዘወትር ከሰው የሚጣላና የሚደባደብ።

አደባደበ ግ አጣላ፥ አማታ።

አስደበደበ ግ አስመታ፡ አስቀጠቀጠ።

ደበደበ² ግ 1. ጠቀመ፡ ጣፈ፡ ደረተ። 2.ደፈነ፡ መረገ፡ ቆረቆረ (የእቃ ሽንቁርን)።

ደባደቦ ስ የተጣጣፈ፡ ድሪቶ።

ድብድብ ቅ ሽንቁሩ በሰም፡ በሙጫ፡... የተደፈነ የሸክላ እቃ።

***ደበደበ**

ድብድብ ስ መዘርዘር፡ ፍሬ መያዝ የጀመረ የአገዳ ወይም የብር እህል (ፍሬው ከድብድብ ደረጃ ሲያልፍ ሶመርቃ ይባላል)።

ተንደበደበ ግ አተረ፡ አበጠ፥ ጉብጉብ አለ (በሰውነት ላይ)።

አደበደበ ግ ፍሬ መያዝ ጀመረ (የገዳ ወይም የብር እህል)።

አንደበደበ ግ ሰውነትን አጉረበረበ፡ እትር እትር እንዲል አደረገ።

ደቡብ ስ በሰሜን ትይዩ የሚገኝ የመሬት አቅጣጫ ፡ የሰሜን ተቃራኒ።

የደቡብ ዋልታ ስ በደቡብ አቅጣጫ ያለው የምድር ጫፍ ።

ደቡብ ምስራቅ ስ በደቡብና በምስራቅ መካከል የሚገኝ አቅጣጫ።

ደቡብ ምእራብ ስ በደቡብና በምእራብ መካከል የሚገኝ የመሬት አቅጣጫ።

ደቡባዊ ቅ በስተደቡብ በኩል ያለ፡ የሚገኝ።

ደባ "***ደበየ**²" ስር ተመ.

ደባለቀ(ደበለቀ) ግ ቀላቀለ፡ ቀየጠ፡ ዘነቀ።

ድብልቅ ቅ ቅልቅል፥ ቅይጥ።

ደብለቅ አለ ግ ተደባለቀ፡ አብሮ ሆነ፥ ተቀላቀለ (ከሰልፈኛ፡ ከተሰብሳቢ፡ ከለቀስተኛ፡... ጋር)።

ደበላለቀ ግ 1. ቀያየጠ፡ ቀላቀለ። 2.አመሰቃቀለ፡ አተረማመሰ።

ድብልቅልቅ ቅ 1. ቅይጥይጥ፥ የተደበላለቀ። 2. ትርምስምስ፥ ዝብርቅርቅ።

ድብልቅልቅ ያለ ቅ በጣም ከፍተኛ የሆነ (ጠብ፥ ድግስ፡...) ።

ተደበላለቀ ግ ተቀላቀለ፡ ተቀየጠ ።

ተደበላለቀ ግ 1. ተቀያየጠ፡ ተቀላቀለ። 2.ተመሰቃቀለ፡ ተተረማመሰ ተረበሸ።

አደባለቀ ግ 1.ቀላቀለ፡ቀየጠ። 2.አተራመሰ፥ በጠበጠ።

ደባል "**ደበለ**" ስር ተመ.

ደባሪ "**ደበረ**³" ስር ተመ.

ደባቃ "**ደበቀ**" ስር ተመ.

ደባባ "**ደበበ**" ስር ተመ.

ደባያት¹ "***ደበየ**¹" ስር ተመ.

ደባያት² "**ደበያት**¹" ን ተመ.

ደባይ¹ "***ደበየ**¹" ስር ተመ.

ደባይ² ስ መረሬ አፈር ወይም መሬት።

ደባይ³ ስ 1. ትልቅ ነጋሪት። 2. የከበሮ አፍ (ሰፊው ወገን)።

ደባደቦ "**ደበደበ**²" ስር ተመ.

ደብር "**ደበረ**" ስር ተመ.

ደብሳሳ "***ደበሰሰ**" ስር "***ደበሰሰ**" ን ተመ.

ደብተራ "**ደበተረ**" ስር ተመ.

ደብተር ስ 1. በፅሁፍ ማስታወሻ ለመያዝ የሚያገለግል፡ የተለያየ ቅርፅና መጠን ያለው፡ በመፅሃፍ ወይም በጥራዝ መልክ የሚዘጋጅ ወረቀት። 2. የባለቤትነት መታወቂያ ወይም ሊብሬ፡ መንጃ ፈቃድ፡ የመሳሰሉና በአነስተኛ ጥራዝ የተዘጋጀ ህጋዊ ሰነድ።

ደብዛ ስ 1. መለያ ምልክት፥ መልክ። 2.አድራሻ። *ደብዛው ጠፋ።*

ደብዛዛ "**ደበዘዘ**" ስር ተመ.

ደብያት "**ደባያት**¹" ን ተመ.

ደብዳቤ “ደበደበ^1” ስር ተመ.

ደብዳቤ ስ በፅሁፍ የሚተላለፍ ሰላምታ፣ መልእክት፣ ትእዛዝ፣...

ደቦ ስ በልመና ወይም በወንፈል መልክ ሰዎች ተሰባስበው ለአንድ ግለሰብ የሚያከናውኑት ስራ፣ ጅጌ፣ ወንፈል።

***ደቦለቦለ “ደበለበለ”** ን ተመ.

ደቦል ስ 1. የአንበሳ ግልገል። 2. አካሉ ፍርጥም ያለ የሰው ወይም የእንስሳ ልጅ።

ደቼ ስ አፈር።

ደቼ ብላ አፈር ብላ።

ደቸኛ ስ 1. ባለመሬት፣ ባላባት። 2. እውቅ ሰው።

ደነሰ ግ በሙዚቃዊ ስልት እየተመራ ማራኪ የሆነ አካላዊ እንቅስቃሴ አደረገ፤ ተወዛወዘ፣ ጨፈረ።

ዳንስ ስ ከሙዚቃ ጋር በሚስማማ መልክ የሚደረግ አካላዊ እንቅስቃሴ፤ ስልታዊ ውዝዋዜ።

ዳንሰኛ ስ የዳንስ ባለሙያ።

አስደነሰ ግ አስጨፈረ። *ሙዚቃው በደንብ አስደነሰን።*

***ደነሰረ**

ደንሳራ(ድንስር) ቅ ሰነፍ፣ ውዝፍ።

ድንስር አለ ግ ተደነሰረ።

ተደነሰረ ግ ተመቻችቶ ተቀመጠ፣ ተወዘፈ።

ደነቀ ግ ገረመ። *ቅዳሴን ስሰማ በጣም ደነቀኝ።*

ድንቅ ቅ ግሩም፣ እፁብ።

ተደነቀ ግ 1. ተገረመ፣ እፁብ አለ። 2. ግሩም፣ እፁብ ተባለ፤ ከፍተኛ አድናቆት ተሰጠው።

ተደናቂ ቅ ግሩም የሆነ፣ ከፍተኛ ዝና ያለው።

አደነቀ ግ ግሩም፣ እፁብ አለ፣ አሞገሰ፤ አመሰገነ።

አድናቂ አሞጋሽ፣ አወዳሽ።

አድናቆት ስ 1. ምስጋና፣ ሙገሳ። *አድናቆትን አገኘ።* 2.የመገረም፣የመደነቅ ስሜት።

አዳነቀ ግ (ዘይ.) አሟሟቀ፤ አጋነነ(ነገርን)።

አዳናቂ ቅ ነገር አጋኖ፣ ሞቅ አድርጎ የሚያወራ።

አስደነቀ ግ አስገረመ፣ እፁብ አሰኘ።

አስደናቂ ቅ አስገራሚ፣ እፁብ ድንቅ የሆነ።

ደነቀረ ግ 1. መዝጊያን እንዳይከፈት ከውስጥ በኩል በአጠና፣ በድንጋይ፣... ደገፈ፣ ዘጋ፤ ሸጎረ። 2. መሰናክል፣ እንቅፋት የሚሆን ነገር አስቀመጠ፣ ጋረጠ። 3. ከተተ፣ ሰካ፣ ቀረቀረ።

መደንቀሪያ ስ የመዝጊያ መቀርቀሪያ፤ መሸጎሪያ (ድንጋይ፣ እንጨት፣...)።

ደንቃራ ስ 1. የገዛ ራስን በሽታ ወደ ሌላ ሰው በማስተላለፍ መዳን ይቻላል በሚል እምነት ብዙውን ጊዜ በመንገድ ላይ የሚጣል እንደሎሚ፣ እንቁላል፣ ቂጣ ያለ የሟርት አይነት። 2.መሰናክል፣ እንቅፋት።

ተደነቀረ ግ 1.ተቀረቀረ፣ ተሰካ። 2.ተጋረጠ።

***ደነቀፈ**

ደነቀፈ(ደንቃፋ) ቅ ሰንካላ፣ ወልካፋ።

ደንቀፍቃፋ(ድንቅፍቅፍ) ቅ ወልከፍካፋ፤ ሰንከልካላ።

ተደነቃቀፈ ግ ተወለካከፈ፤ ተሰነካከለ።

ተደናቀፈ ግ ተወላከፈ፤ ተሰናከለ፣ እንቅፋት አገኘው።

አደነቃቀፈ ግ አወለካከፈ፤ አሰነካከለ።

አደናቀፈ ግ 1. አወላከፈ፣ አሰናከለ፣ አነቀፈ። 2. እንዳይካሄድ፤ እንዳይሳካ አደረገ።

አደናቃፊ ቅ መሰናክል፣ እንቅፋት የሆነ።

ደነቆለ ግ ጠነቆለ፣ ዘነቆለ፣ አነቆረ፤ ወጋ።

መደንቆያ ስ ማንቆሪያ፣ መውጊያ።

ደነቆረ ግ 1. ጆሮው ተደፈነ፣ ድምፅ አልሰማው አለ። 2. ጃለ፤ ፈዘዘ፣ ነሆለለ። 3. እውቀት፣ ስልጣኔ የሌለው ሆነ።

ደንቆሮ ቅ 1. ጆሮው የማይሰማ። 2. (ዘይ.) ደደብ፣ እውቀት የሌለው። 3. ያልተማረ።

ደንቆሮ እንስራ ስ ጆሮው የተሰበረ ወይም ጆሮ የሌለው እንስራ።

ደንቆሮ ወፍጮ ስ የሚለበና ያልተወቀረ ባህላዊ የእጅ ወፍጮ።

ድንቁርና ስ 1. የጆሮ አለመስማት። 2. ደደብነት፣ እውቀት የለሽነት። 3. ማይምነት፤ ኋላቀርነት።

ተደናቆረ ግ 1. ደነቆረ። 2. እያንዳንዱ በየበኩሉ እየጮሀ ለመደማመጥ በማያመች ሁኔታ ባንድ ጊዜ አወራ፣ ተነጋገረ።

አደነቆረ ግ በሰው ጆሮ ላይ አለአግባብ ጮሀ።

አደናቆረ ግ 1. አጯጯሀ፤ አሰፋሰፈ። 2. አታለለ፣ አወናበደ።

ደነበረ ግ 1. ደነገጠ፣ ፈራ፣ ገረገረ። 2. በረገገ፣ ዘለለ፤ ወገሸ፤ ሸሸ።

ደንባራ ቅ ድንጉጥ፣ በርጋጊ።

ደንባራ ዝ.ከ.

***ደነበረ**

ደንባራ (ደምባራ) ቅ 1. በትክክል ማየት፤ ማድረግ... የማይችል። 2. (ስድብ) እውር።

ድንብርብር(ደንበርባራ) ዝ.ከ.

ድንብርብር አለ ግ ተደናበረ።

ተደናበረ ግ 1. ተደናገረ፡ ግራ ተጋባ። 2. ታወረ፤ በትክክል ማየት ተሳነው።

አደናበረ ግ 1. አደናገረ፡ ግራ አጋባ። 2.አሳወረ፥ አጠናበረ።

*ደነበረ^2

ድንበር (ድምበር) ስ 1. የአንድ የተወሰነ የመሬት ወይም የቦታ ክልል(ወሰን፡ ድካ፡...) ከየት እስከ የት እንደሆነ ለማመልከት ይረዳ ዘንድ በመሬቱ ወይም በቦታው ጠርዝ ላይ እንዲሆን የሚደረግ ምልክት ወይም ተፈጥሮአዊ የሆነ ድንጋይ ፥ ኮረብታ፥ ወንዝ፥...። 2. የአንድ አካል ጠረፍ፥ ጠረዝ፥ ዳርቻ፥ ወሰን፥ ድካ፥...። 3. ገደብ፡ መጠን፡ ልክ። *ንግግርህ በልክ ይሁን፤ ድንበር አትለፍ።*

ድንበርተኛ (ድምበርተኛ) ስ የተወሰነ የቦታ ክልልን የሚያጎራብት መሬት፡ ቦታን አዋሳኝ፥ ወሰንተኛ።

ደነበሸ ግ ሻገተ፥ ታመገ(እህል)።

ደንበሾ ስ ሻጋታ።

ደነበቀ ግ መጥለቂያን ወይም መቅጃን ከውሃ ወይም ከፈሳሽ ነገር ውስጥ እየጠለቀ ቀዳ፡ ጠለቀ።

ደነበዘ 1. ፈዘዘ ፡ ደነዘዘ፥ ደነገዘ። 2. ጨለመ፥ ጠቆረ።

ደነበዝ(ደንባዛ) ቅ 1. ፈዛዛ፥ ደንጋዛ። 2. ጥቁር፥ ጨፍና።

ደነባ ግ ሀግ፥ ደንብ ሰራ፥ አበጀ፥ አወጣ።

ደንብ (ደምብ) 1. የተወሰነ ህግ፡ ድንጋጌ፥ ስርአት። 2. ወግ፡ ልማድ።

ደንብ አወጣ ደነገገ ፤ ስርአት፥ ህግ አበጀ፥ ሰራ።

የደንብ ልብስ ስ 1. ወታደሮች ከሌላው ተለይተው የሚታወቁበትና በስራ ላይም ሆነ በሌላ ጊዜ የሚለብሱት ልብስ። 2. በአይነቱ፥ በአሰራሩና በመልኩ ተመሳሳይ የሆነ በአንድ ት/ቤት ወይም ድርጅት ውስጥ የሚገኙ ሰዎች የሚለብሱት አንድ አይነት የሆነ ልብስ፡ ዩኒፎርም።

ደንበኛ(ደምበኛ) ቅ 1. ዋና፡ ዋነኛ። 2. ጥሩ፥ ሁነኛ፥ አይነተኛ። 3. መደበኛ። *ደንበኛ ወታደር።* 4. ስ አንድን ጉዳይ ወይም የጋራ ጥቅምን በተመለከተ ግንኙነቱን አዘውትሮ ከተወሰነ ግለሰብ ወይም ድርጅት ጋር የሚያደርግ ግለሰብ ወይም ድርጅት።

*ደነከረ

ደንካራ ቅ ወንካራ፥ ወልጋዳ፥ ወልካፋ።

ደንከር ደንከር አለ ግ ወንከር ወንከር፡ ወልገድ ወልገድ አለ። (በአካሄድ)።

ተደናከረ ግ ተወናከረ፡ ተወላገደ።

አደናከረ ግ አወናከረ፡ አወላገደ።

ደነዘ ግ 1. ጠረሰ፡ ዱለዱመ፥ ስለት አልባ ሆነ (የስለት መሳሪያ)። 2. (ዘይ.) ፈዘዘ፡ ደደበ፡ ደነቆረ፤ ንቃት፡ ቅልጥፍና አጣ።

ደነዝ(ደናዛ) ቅ 1. ጠራሳ፡ ዱልዱማ፡ ስለት የለሽ። 2. (ዘይ.) ንቃት፥ ቅልጥፍና የሌለው፥ ደደብ።

ደነዘዘ ግ በድን ሆነ፥ ደነገዘ፥ ፈዘዘ፥ ንቃት ቅልጥፍና፥ አጣ።

ደነዘዝ(ደንዛዛ) ቅ ፈዛዛ፡ በድን።

አደነዘዘ ግ በድን አደረገ፤ አደነገዘ፡ አፈዘዘ፥ ንቃት፥ ቅልጥፍና አልባ አደረገ።

ማደንዘዣ ስ አካልን ወይም አእምሮን የሚያፈዝ መድሃኒት፤ እፅ።

አደንዛዥ ቅ የሚያፈዝ (አካልን፥ አእምሮን)።

አደንዛዥ እፅ ስ ለጊዜው ስሜትን የማነቃቃትና የማስደሰት ባህርይ ያለው፡ እየዋለ እያደር ግን የተጠቃሚውን (የሱሰኛውን) አእምሮ የሚያፈዝና የሚያደነዝዝ፤ ሰውነትን የሚያገል፥... እንደ ሃሺሽ ያለ ሱስ አስያዥ እፅ።

ደነዝ "ደነዘ" ስር ተመ.

ደነደነ ግ ወፈረ።

ደንዳና ቅ ወፍራም።

ደንዳኔ ስ ትልቅ አንጀት።

*ደነገረ

ደንጋራ ቅ ደንባራ፥ ግራ የሚገባው፤ የተረጋጋ አስተውሎቱትና ነገሮችን ፈጠን ብሎ የመረዳት ችሎታ የሚያጥረው።

ድንግርግር አለው ግራ ተጋባ።

ተደነጋገረ ግ 1. ተደነባበረ፡ ግራ ተጋባ። 2.ተምታታ፥ ተዘበራረቀ።

ተደናገረ ዝ.ከ.

አደነጋገረ ግ 1. አደነባበረ፥ ግራ አጋባ። 2.አምታታ፥ አሳሳተ፥ አዘበራረቀ፡ አጭበረበረ።

አደናገረ ዝ.ከ.

አደናጋሪ ቅ አጭበርባሪ፡ አምታች፡ አውቆ አሳሳች።

ደነገዘ ግ 1. እንደ መጨለም አለ፤ ለአይን ያዘ። 2. ፈዘዘ፥ ደከመ።

ደንገዝ ቅ ፈዛዛ።

ድንግዝግዝ አለ ግ ጨልምልም አለ።

አደነገዘ ግ 1.አደነዘዘ፡ አፈዘዘ። 2. አደከመ።

አፈዘዘ።

ደነገገ ግ ወሰነ፤ ህግ፡ ደንብ አወጣ።

ድንጋጌ ስ ህግ፡ ደንብ፥ ስርዓት።

ተደነገገ ግ ህግ፡ ደንብ ወጣ ወይም ተሰራ።

ደነገጠ ግ 1. ድንገት አእምሮው ተረበሸ፥ ታወከ (አንድ ነገር በማየቱ ወይም በመስማቱ፡... የተነሳ)። 2. ፈራ፡ ራደ።

ደንጋጣ ቅ ስጉ፡ ፈሪ፥ በርጋጋ።

ድንጉጥ ቅ 1. ስጉ፡ ፈሪ። 2. ሽቁጥቁጥ፡ ትሁት።

ድንጋጤ ስ ድንገት የሚያጋጥም ፍርሃት ወይም መረበሽ።

ተደናገጠ ግ ደነገጠ፥ ፈራ።

ደነጎረ^{1} ግ በደንጎራ ቆፈረ፤ ደቀደቀ፡ ማሰ (መሬትን)።

መደንጎሪያ ስ ዛቢያው ቀጥ ያለና ወፍራም ሆኖ በጫፉ ላይ ማረሻ ወይም መጥረቢያ መሰል ዶማ የተዋደደበት መቆፈሪያ፥ ደንጎራ።

መደንጎሪያ

ደንጎራ ዝ.ከ.

ደነጎረ^{2} ግ 1. መተላለፊያን ወይም በርን በእንጨት፡ በድንጋይ፥... ዘጋ፡ አገደ። 2. (ዘይ.) አንድን ነገር ካለቦታው አስገባ። 3. አባባ ጎባጣ፥ ጉራንጉር አደረገ።

ድንግርግር ስ ጉራንጉር፡ ድንጋይ የበዛበት ቦታ።

ድንግርግር አለ ግ ተደነንጎረ።

ድንግርግር አደረገ ግ አደነንጎረ።

ተደነንጎረ ግ ተመሰቃቀለ፡ ተደበላለቀ፥ ተተረማመሰ።

ተደናጎረ ዝ.ከ.

አደነንጎረ ግ አመሰቃቀለ፡ አዘበራረቀ፡ አተረማመሰ።

አደናጎረ ዝ.ከ.

ደነፈቀ ግ በብዛት እንባ እያፈሰሰ አለቀሰ፤ ተንሰቀሰቀ፡ ነፈረቀ።

አስደነፈቀ ግ በጣም አስለቀሰ፤ አነፋረቀ።

ደነፋ ግ 1. እየተንጎራደደ የፉከራ ቃል አሰማ። 2. ዛተ፥ ፎከረ።

ደንፊ ቅ 1. ዛቺ፥ ፎካሪ ። 2. ጉረኛ።

ድንፋታ ስ 1. ፉከራ ። 2. ዛቻ።

ደናዛ "ደነዘ" ስር ተመ.

ደናግል "ድንግል" ን ተመ.

ደን ስ ጫካ፥ ዱር (ዛፍ፡ ቁጥቋጦ፡... በብዛት የሚገኝበት)።

ደንሳራ "*ደነሰረ" ስር ተመ.

ደንሴ(ደንሶ) ቅ አመለ ልስልስ፥ ገራም።

ደንቀፍቃፋ "*ደነቀፈ" ስር ተመ.

ደንቃራ "ደነቀረ" ስር ተመ.

ደንቃፋ "*ደነቀፈ" ስር **"ደነቀፍ"**ን ተመ.

ደንቆሮ "ደነቆረ" ስር ተመ.

ደንበርባራ "ደነበረ" ስር **"ድንብርብር"**ን ተመ.

ደንበሸ "ደነበሸ" ስር ተመ.

ደንበኛ "ደነባ" ስር ተመ.

ደንበጃን "ደምበጃን" ተመ.

ደንባሪ "ደነበረ" ስር ተመ.

ደንባራ^{1} **"ደነበረ**^{1}**"** ስር ተመ.

ደንባራ^{2} **"ደነበረ**^{2}**"** ስር ተመ.

ደንባዛ " ደነበዘ" ስር ተመ.

ደንብ "ደነባ" ስር ተመ.

ደንታ ስ ግድ፥ ቁብ።

ደንታ ቢስ ቅ ግድ የለሽ።

ደንታ የለውም ግድ የለውም፥ አይጨነቅም።

ደንካራ "*ደነከረ" ስር ተመ.

ደንዛዛ "ደነዘዘ" ስር **" ደነዘዝ"** ን ተመ.

ድንደሮ^{1} ቅ ወፍራም፥ ጠብደል ።

ደንደሮ^{2} ስ የኮሸሽላ አይነት።

ደንደስ ስ 1. ማጅራት፡ ጫንቃ። 2. ከማጅራት እስከ ጭራ የሚዘልቅ ረዥምና ባለብዙ አጥንት፥ አከርካሪ።

ደንደሳም ቅ ማጅራቱ፥ ጫንቃው የወፈረ።

ደንዳ(ዳንዳ) ስ ማማ።

ደንዳና "ደነደነ" ስር ተመ.

ደንዳኔ ዝ.ከ.

ደንገሳሳ ስ በሽምጥና በሶምሶማ መካከል ያለ የፈረስ ግልቢያ አይነት።

ደንገል ስ በወንዝ ዳርቻ፥ ውሃ በተኛበት ቦታ የሚበቅል፡ እንደ መቃ ያለና ለታንኳ የሚያገለግል ወፍራም ሳር።

ደንገሎ ስ ለውሻ፥ ለበቅሎ፥... መኖ እንዲሆን ዱቄቱ ከነአሰሩ ተቦክቶ የሚዘጋጅ ቂጣ።

ደንገጡር(ደንገጥር) ስ ቀደም ባለው ጊዜ የእመቤቷን ጌጥ ተሸክማ እመቤቷን ትከተል ወይም ታጅብ የነበረች ሴት።

ደንገጥር^{1} ስ በሸማ ጥበብ ዳርና ዳር በክፈፍነት የሚጣል ጥለት።

ደንገጥር^{2} **"ደንገጡር"** ን ተመ.

ደንጊያ "ድንጋይ" ን ተመ.

ደንጋራ "ደነገረ" ስር ተመ.

ደንጋጣ "ደነገጠ" ስር ተመ.

ደንግ ስ ከብር፡ ከወርቅ፡… የሚሰራ የጌጥ አይነት።

ደንጎለጥ(ደንጎሊጥ) ቅ 1. አመሉ አስቸጋሪና መጥፎ የሆነ (ሰው)። 2. ትምህርት የማይገባው፡ አእምሮው ትምህርት የማይቀበል (ሰው)።

ዶንጎላጉል(ደንጎለት) ቅ አባጣ ጎባጣ፡ አስቸጋሪ፡ አጉል፡ የማይረባ።

ደንጎሎ ስ የአደንጓሬ አይነት፡

ደንጎራ "ደነጎረ¹" ስር ተመ.

ደንፋ "ደነፋ" ስር ተመ.

ደከመ ግ 1. ሃይል፡ አቅም፡ ብርታት አጣ፡ ጉልበቱ አለቀ። 2. ፈዘዘ፡ ሃይሉ ቀነሰ። 3. ዛለ፡ ተልፈሰፈሰ። 4. ታከተ፡ ሰለቸ። 5. ሰነፈ። 6. አረጀ። 7. ጣር ያዘው፡ ለሞት ተቃረበ፡ 8. ብዙ ጣረ፡ ጋረ፡ ለፋ።

ደካማ ቅ 1. አቅመቢስ። 2. ሰነፍ። 3. አካለ ስንኩል። 4. ልል፡ ጠንካራ ያልሆነ። 5. የአስተሳሰብ ብቃት የሌለው፡ አስተሳሰቡ እንጭጭ የሆነ። 6. ጥራት፡ ብቃት፡… የሌለው። *የሰራው ስራ ደካማ ነው።*

ደካማ ጎን እንከን፡ ጉድለት (የአስተሳሰብ፡ የአድራጎት)።

ድኩም ቅ 1. ደካማ፡ ሰነፍ። 2. (ብ.ቁ. **ድኩማን**) አካለ ስንኩል።

ድካም ስ 1. ሃይል፡ አቅም፡ ብርታት ማጣት። 2. ልፋት፡ ጥረት።

የድካም ዋጋ ስ ለስራ፡ ለአገልግሎት የሚደረግ ክፍያ።

ድክመት ስ 1. ሃይል፡ አቅም፡ ብርታት ማጣት። 2. ስንፍና። 3. እንከን፡ ጉድለት (የአስተሳሰብ፡ የአድራጎት)።

ተደከመ ግ ጥረት ተደረገ። *ላልተሳካም እንጂ ለዚህ ሃገር ብዙ ተደክሞ ነበር።*

ተዳከመ ግ 1. ሃይል፡ አቅም፡ ብርታት አጣ። 2. ዛለ፡ ተልፈሰፈሰ። 3. ሰነፈ። 4. አረጀ። 5. ጣር ያዘው፡ ለሞት ተቃረበ። 6. ቀዘቀዘ፡ እንቅስቃሴው ቀነሰ። *ዝሆኑ ተዳከመ።*

አደከመ ግ 1. አለፋ። 2. ብርታት፡ ሃይል አቅም አሳጣ።

አድካሚ ቅ አሰልቺ፡ አልፊ፡ አዋኪ (ስራ፡…)።

አዳከመ ግ 1. ሃይል፡ ብርታት እንዲያጣ ወይም እንዲደክም አደረገ። 2. በጥሩ ሁኔታ እንዳይሰራ፡ እንዳይንቀሳቀስ፡… አደረገ። *ድርጅቱን ያዳከመ ተባረረ።*

3. አሳነፈ።

ደከረ ግ 1. አቀረበ፡ አዘጋጀ፡ ደቀነ። 2. አዘገበ፡ አነጣጠረ።

ተደከረ ግ 1. ቀረበ፡ ተዘጋጀ፡ ተደቀነ። 2. ተዘገበ፡ ተነጣጠረ።

ደከነ ግ በትንሽ በትንሹ ከመረ፡ ቆለለ፡ (የታጨደ ሰብልን)።

ድክን (ድክን) ስ አነስተኛ ክምር (የሰብል)።

ደከከ ግ 1. አጠረ። 2. አጭርና ወፍራም ሆነ።

ደኪክ ቅ አጭርና ወፍራም።

ተንዳከከ ግ 1. ደኪክ ሆነ። 2. ተንቆረሰሰ፡ ፍጥነት አጣ (በአካሄድ)።

አንዳከከ ግ አንቆረሰሰ፡ ፍጥነት አሳጣ (በአካሄድ)።

ደከደከ ግ ራሰ፡ በሰበሰ።

ደከደክ (ደከዳካ) ቅ የራሰ፡ የበሰበሰ።

***ደከደከ**

ዶኬ ስ 1. ቅመምና ቅባት የሌለበት መረቅ ወጥ። 2. ወፍራም የሽሮ ወጥ።

ደክ ደክ አለ ግ ተንደከደከ።

ተንደከደከ ግ 1. ፈላ (ሽሮ ወጥ)። 2.ወፍራም ሽሮ ሲንተከተክ የሚያሰማውን አይነት ድምፅ አሰማ።

አንደከደከ ግ አፈላ፡ ቀቀለ (ሽሮን)።

ደከደከ "ደከደከ" ስር ተመ.

ደካ¹ ግ ወሰን፡ ክልል፡ ድንበር አበጀ።

ዱካ¹ ስ ፈለግ፡ ኮቴ፡ ፋና።

ድካ ስ 1. ወሰን፡ ክልል። 2. የወሰን፡ የክልል ምልክት (ድንጋይ፡ እንጨት፡…)።

ተዳካ ግ ተዋሰነ፡ ተከለለ።

ደካ² ግ 1.ገሰለጠ፡ አለፋ። 2. ደቃ፡ መታ።

ደኮ ስ የለፋ ደበሎ፡ ድብዳብ።

ደካማ "ደከመ" ስር ተመ.

ደካካ "ደከከ" ስር ተመ.

ደከዳካ "ደከደከ" ስር "ደከደክክ ን ተመ.

ደኳኳ(ድኳ) ስ 1. የእንጨት ትራስ፡ ብርኩማ። 2. በእጃቸው እየተረዱ አካለ ስንኩሳን የሚጠቀሙበት የእጅ ብርኩማ ወይም መንፏቀቂያ። 3. ለመቀመጫነት የሚያገለግል በርጩማ።

ደወለ ግ 1. ደወልን መታ እንዲቃጨል፡ የደወል ድምፅ እንዲሰጥ አደረገ። 2. የደወል ድምፅ አሰማ። 3. መታ፡ ደቃ፡ ደለቀ (በኩጢ)። 4. የስልክ ጥሪ አደረገ፡ በስልክ አነጋገረ። 5. በነፍስ ግዳይ ወይም በሌላ ከፍተኛ ጠብ ምክንያት ቂም

በቀል ከያዙበት ሰዎች ጋር እንዲያስታርቁት የቤተክርስቲያን ደወል በመደወል ካህናትን ተማጸነ፣ ለመነ።

ደወል ስ 1. ከእንጨት ወይም ከብረት ወይም ከድንጋይ፥... በተለያየ ቅርፅ ተሰርቶ በብረት ወይም በድንጋይ፣... ሲመቱት ድምፅ የሚሰጥ፣ ለጥሪ የሚያገለግል መሣሪያ (ብዙውን ጊዜ በቤተ ክርስቲያን፣ በት/ቤት የሚገኝ)። 2. በኤሌክትሪክ ኃይል የሚሰራ፣ በጣት ሲጫኑት (የኤሌክትሪኩን ኡደት መስመሩን በማገናኘት) ድምፅ የሚሰጥ መጥሪያ (በቢሮ፣ በመኖሪያ ቤት፣...የሚገኝ)።

ደዋይ ቅ 1. ተግባሩ በየወቅቱ ደወል መደወል፣ የደወል ጩኸት ማሰማት የሆነ (ሰው)። 2. የስልክ ጥሪ አድራጊ (ሰው)።

ተደወለ ግ 1. የደወል ድምፅ ተሰማ፤ ደወል ተመታ። 2. የስልክ ጥሪ ተደረገ።

ተዳወለ ግ ተማታ፣ ተጻለቀ /በቡጢ፣.../።

ደወረ ግ ጠመጠመ፣ ጠቀለለ፣ አጠነጠነ (ፈትልን፣ ክርን፣...)።

መደወሪያ(ማዳወሪያ) ስ ፈትልን፣ ክርን፣... ለማጠንጠን የሚያገለግል ባህላዊ የሸማኔ እቃ።

ደዋሪ(አዳዋሪ) ስ ድውር አጠንጣኝ።

ድውር ስ በቀሰም ላይ የተጠመጠመ፣ የተጠቀለለ ፈትል፣ ክር፣...።

ተደወረ ግ ተጠመጠመ፣ ተጠቀለለ፣ ተጠነጠነ (ፈትል፣ ክር፣...)።

ተዳወረ ዝ.ክ.

አዳወረ ግ ደወረ።

ማዳወሪያ "**ደወረ**" ስር "**መደወሪያ**"ን ተመ.

አዳዋሪ "**ደወረ**" ስር "**ደዋሪ**"ን ተመ.

ደዋይ "**ደወለ**" ስር ተመ.

ደዌ(ዱያት) ስ 1. ህመም። 2. የቆዳ በሽታ።

ደዌ ስጋ ስ ቁምጥና።

ዱያታም ቅ (ስድብ) የተለያየ በሽታ ያለበት (ሰው)።

ድውይ ቅ 1. (ስድብ) ቆማጣ። 2. በሽተኛ። 3. (ዘይ.) በጣም አጭር (ሰው)።

ደውዳዋ ቅ አውደልዳይ፣ አደዝዳዥ።

ደዘደዘ ግ 1. መታ፣ ጠለዘ። 2. ወቀጠ።

***ደዘደዘ**

ደዘደዥ ቅ አውደልዳይ፣ አደሽዳሽ፥ ስራ ፈት።

አደዘደዘ ግ አውደለደለ፣ አደሸደሸ፣ ስራ ፈታ።

አደዝዳዥ ቅ (ስድብ) አውደልዳይ፣ ስራ ፈት።

ደየነ ግ ኮነነ፣ ለመከራና ለስቃይ ዳረገ።

ደይን ስ የመከራና የስቃይ ቦታ፣ ሲኦል።

ደይን(ደይኔን) አየሁ ተሰቃየሁ፣ ተንገላታሁ።

ደዶሆ ስ በቆላና በወይናደጋ አካባቢ የሚበቅል ትናንሽ ፍሬዎችን የሚያፈራ አነስተኛ ዛፍ።

ደደረ ግ ጠጠረ፣ ጠነከረ (ብዙውን ጊዜ የእጅ መዳፍ፣ ውስጥ እግር፣...)።

ድድር ቅ ጥጥር፣ ጠንካራ።

ደደቀ ግ በመደደቂያ መሬቱን እየወጋ ቆፈረ፣ አፈሩን ማሰ፣ ንሉን ገለበጠ፣ ደነገረ።

መደደቂያ ስ ሹል የሆነ መንታ ጫፍ ያለው ብረት የተዋደደበት መቆፈሪያ፣ መደንገሪያ።

ድድቅ ቅ በመደደቂያ የተቆፈረ (መሬት)።

መደደቂያ

ደደቆ ስ 1. ኩልኩሌት ። 2. የበግ አንገት የሚያሳብጥ በሽታ።

ደደበ ግ 1 ደነዘ፥ እውቀት የማይገባው ሆነ። 2. በድን ሆነ፣ ደነዘዘ (ሰውነት)።

ደደብ ቅ 1. (ስድብ) ደነዝ፣ እውቀት የማይገባው። ስ 2. ቆዳ ሲገፈፍ ከቆዳው ላይ ተለጥፎ የቀረ ስጋ።

ደጀ ሰላም "**ደጅ**" ስር ተመ.

ደጀን ስ በጦርነት ከሚሰለፈው ወገን (ብዙውን ጊዜ የጦር ሃይል) ድጋፍ ሰጭ ወይም ተጠባባቂ እንዲሆን ከበስተኋላ በኩል የሚሰለፍ ሃይል።

ደጅ ስ 1. ከቤት ውጭ ያለ ቦታ። 2. የቤት በር፣ መግቢያ። *ደጁን ዘጋው።*

ደጅ ወጣ 1. ለመፀዳዳት ወደ ጓሮ ሄደ። 2. ከህመሙ አገግሞ ደጅ ለደጅ መንቀሳቀስ ጀመረ። 3. የደረሰበትን ግፍ ለመበቀል ሸፈተ። 4. ይፋ ሆነ። *ነገሩ ደጅ ወጣ።*

ደጅ ወጣች 1. ግብር ውሃ ወጣች፥ ለመፀዳዳት ወደ ጓሮ ሄደች። 2. ከወሊድ በኋላ የሚያስፈልጋትን የእረፍት ጊዜ ጨርሳ ተነሳች፤ ስራ ጀመረች።

ደጅ ጠና ጉዳዩን እንዲፈፅምለት ወደሚመለከተው ዘንድ እየተመላለሰ እጅ ነሳ፣ ተለማመጠ፥ ልመና አቀረበ።

ደጅ ጠኚ(ደጅ ጠኚ) ስ ጉዳዩን እንዲፈፅምለት ወደሚመለከተው ባለስልጣን ዘንድ እየሄደ የሚለማመጥ፥ እጅ የሚነሳ፣ ልመና የሚያቀርብ ሰው።

ደጅ ጥናት ስ አንድን ጉዳይ ለማስፈፀም ወደሚመለከተው ባለስልጣን ዘንድ እየተመላለሱ ልመና፣ አቤቱታ ማቅረብ፥ መለማመጥ።

ደጅ አስጠና በደጅ ጥናት አጉላላ፥ አለፋ።

ደጇ ሰላም ስ 1. በቤት ወይም በእድሞ መልክ ሆኖ የሚሰራ፥ ወደ ቤተ ክርስቲያን ግቢ ለመግባትና ለመጣት እንደመተላለፊያ የሚያገለግል የቤተክርስቲያን አጥር ዋና በር። 2. ካህናት መክፈልት የሚበሉበትና በቤተክርስቲያን ግቢ ውስጥ የሚገኝ ቤት።

ደጇ ብርሃን ስ ቤተልሄም።

ደጃዝማች(ደጃማች፡ ደጃች) ስ 1.በቀድሞ ጊዜ የጦር የበላይ ሹም የማእረግ ስም። 2.በራስና በፊታውራሪ መካከል ያለ የማእርግ ስም።

ደጃፍ ስ 1. በመዝጊያ የሚከለል የቤት ክፍተት፥ መግቢያና መውጫ። 2. በቤት በር አካባቢ የሚገኝ ቦታ። 3. የቤት መዝጊያ።

ደገለለ ግ በወፍራሙ ጠቀለለ፥ ጠማጠመ።

ደገሌ ስ ማቶት።

ደገመ^1 ግ 1. አንድን ነገር እንደገና መልሶ አደረገ። 2. አከለ፥ ጨመረ። 3. ወደቀ። ፈተና ሳያልፍ በመቅረቱ እነበረበት ክፍል በመቆየት እንደገና እንዲማር ሆነ።

ደጋሚ ቅ ፈተና ሳያልፍ በመቅረቱ እነበረበት ክፍል በመቆየት እንደገና እንዲማር የሆነ።

ደግሞ 1. እንደገና። 2. በተጨማሪ።

ዳግም(ዳግሚያ) ዳግመኛ።

ዳግም(ዳግማይ) ትንሳኤ ስ ከትንሳኤ በኋላ ያለው የመጀመሪያው እሁድ።

ዳግም [አረቄ] ስ በድጋሚ እንዲጣራ ወይም ነጥሮ እንዲወጣ የተደረገ አረቄ።

ዳግመኛ (ዳግሞሽ) ተው.ግ. እንደገና፥ ለሁለተኛ ጊዜ።

ዳግማዊ ቅ ሁለተኛ። *ዳግማዊ ምኒልክ*።

ድጋሚ ተው.ግ. 1. እንደገና፥ ለሁለተኛ ጊዜ። 2. በተጨማሪ።

ደጋገመ ግ አንድን ነገር መላልሶ አደረገ።

ድግግም ስ ተደጋጋሚ፥ የአንድ ድርጊት ምልልስ፥ ተደጋግሞ መሆን፥ መደረግ።

ድግግሞሽ ዝ.ክ.

ተደጋገመ ግ አንድ ነገር ተመላልሶ ተደረገ።

ተደጋጋሚ ቅ ተመላልሶ የሚደረግ፥ የተደረገ።

አደጋገመ ግ አንድ ድርጊት ከተከናወነ በኋላ ተመልሶ እንደገና እንዲደረግ አስፈለገ።

አዳገመ ግ አደጋገመ።

አስደገመ ግ እንደገና (በድጋሚ) አስደረገ።

ደገመ^2 ግ 1. በለሆሳስ አነበበ፥ አነበነበ (ፀሎትን)። 2. ተማረ፥ ጨረሰ (ደዊትን)።

ደገመበት ድግምት አደረገበት።

ደጋሚ ስ በንባብ ፀሎት የሚያደርስ፥ አነብናቢ።

ድጋም ስ በለሆሳስ የሚደረግ ፀሎት።

ድግምት ስ የአስማት መነባንብ።

ድግምተኛ ስ አስማተኛ፥ መተተኛ።

ድግምታም ዝ.ክ.

አስደገመ ግ 1. አስማት አስደረገ። 2.የፀሎት መፅሃፍ እንዲነበብ አስደረገ፥ አስፀለየ። 3. አስተማረ፥ አስጠና (ዳዊትን)።

ደገሰ ግ 1. አሰናዳ፥ አዘጋጀ (ምግብና መጠጥ ወይም ሌላ ነገር ለተጋባዦች)። 2. ጠነሰሰ፥ አዘጋጀ (ሴራ፥ ተንኮል፥...)።

መደገሻ ስ ድግስ የሚዘጋጅበት ገንዘብ፥ ቦታ፥...።

ደጋሽ ቅ ድግስ የሚያዘጋጅ።

ድግስ ስ 1. ለጋብቻ፥ ለሰርግ፥... የሚዘጋጅ ምግብና መጠን። 2. አንድ ነገር ለማከናወን የሚደረግ ዝግጅት።

ተደገሰ ግ ተሰናዳ፥ ተዘጋጀ (ድግስ ወይም ሌላ ነገር)።

ደገነ ግ 1. አጎበጠ (እንደደጋን) ። 2. አዘገበ፥ አነጣጠረ።

ደጋን ስ 1. ለጥጥ፥ ለሱፍ ፀጉር፥... መንደፊያ የሚያገለግል ጅማት የተወጠረበት ጎባጣ እንጨት። 2. እንደ ደጋን ሆኖ የተሰራ የቀስት ማፈናጠሪያ።



ደጋን 1ኛ ፍች

ደጋን እግር ቅ (ሰድብ) የእግሩ ቅልጥም እንደ ደጋን የጎበጠ።

ደጋን ወገብ ቅ ከወደ ወገቡ ጎበጥ ያለ።

ድግን መትረየስ ስ ባለእግር መትረየስ።

ድግን መጋዝ ስ እጀታው በደጋን ቅርፅ የተሰራ መጋዝ።

ደገኛ " **ደጋ**" ስር ተመ.

ደጎኛ " **ደግ**" ስር ተመ.

*ደገዘ (*ደገዘገዘ)

ድግዝግዝታ ስ ጭልምልም ያለ፥ ምሽት።

ድንግዝግዝ አለ ግ ጨለመ።

ደገደገ^1 ግ 1. ከዳ፡ ከሰሰ፥ መነመነ። 2. ፈዘዘ (አይን)።

ደግዳጋ ቅ ከሲታ፡ ከሳሳ።

ደገደገ^2 ግ አደፈ፡ ቸከ።

ደግዳጋ ቅ አዳፋ፡ የቸከ።

***ደገደገ**

ድግ ስ ርዝመቱ ከ25 እስከ 30 ክንድ የሚሆን፥ በቀድሞ ጊዜ ወንዶች ወገባቸው ላይ ይጠመጥሙት የነበረ መታጠቂያ፤ በጣም ረጅም የሆነ መቀነት።

ድግድግ ስ ድግድጋት።

ድግድጋት ስ 1. ወደ ቤተክርስቲያን፥ ወደ ቤተ መንግስት ሲገባ ወይም ክብር ሊሰጠው ወደሚገባ ሰው ዘንድ ሲቀረብ የሚደረግ የተለየየ የሽማ አለባበስ ስርአት። 2. በሃዘን ጊዜ ሴቶች የነጠላቸውን አንዱን ጫፍ በጥለቱ በኩል ወገባቸው ላይ አስረው ሌላውን ጫፍ በትከሻቸው በኩል በማጣፋት የሚያደርጉት የአለባበስ ስርአት።

አደገደገ ግ 1. ሽማውን በድግድጋት አለባበስ ስርአት ለበሰ። 2. (ዘይ.) ሀ. ታጠቀ፥ ተዘጋጀ፥ አሰፈሰፈ (አንድ ነገር ለማድረግ)። ለ. ተለማመጠ፥ አጎበደደ።

አደገደገች አሸረጠች።

አደግዳጊ ቅ (ዘይ.) ተለማማጭ፥ ሽርጉድ ባይ።

አስደገደገ ግ (ዘይ.) አስጨነቀ፥ አስፈራ፡ ሽርጉድ አሰባለ።

አስደግዳጊ ቅ ሃይለኛ፥ አስፈሪ፥ አስጨናቂ፥ ሽርጉድ የሚያስብል።

ደገፈ ግ 1. ድጋፍ ሆነ። 2. ረዳ፥ አገዘ። 3. ቀደም ሲል የተሰነዘረን ሃሳብ መቀበሉን ወይም ትክክለኛ ሃሳብ መሆኑን በማጠናከር ተናገረ፥ ሃሳብ ሰጠ።

ደገፋ ስ 1.ወጋግራ፥ ምሰሶ። 2. የአልጋ ሸንኮር ወይም እግር።

ደገፋ ስ ቃሊብ፥ የወንዝ ዳርና ዳር። *ወንዙ ከአፍ እስከ ደገፉ ሞልቷል።*

ደጋፊ ቅ ረዳት፥ አጋዥ።

በድግፍግፍ በብዙ ድጋፍ፥ በእርዳታ።

ድጋፍ ስ 1. እርዳታ፥ እገዛ። 2. አንድ አካል ባለበት ቦታ ሳይነቃነቅ ወይም ሳይወድቅ እንዲቆይ ጥንካሬ የሚሰጥ ሌላ አካል። 3. መከዳ፥ ትራስ። 4. ማጠናከሪያ፥ ተጨማሪ ሃይል።

የድጋፍ ሰልፍ ስ አንድን አቋም በመደገፍ የሚደረግ ሰልፍ።

ተደገፈ ግ 1.ተረዳ፡ ታገዘ፡ ድጋፍ ተደረገለት። 2. ድጋፍ አገኘ።

ተደጋገፈ ግ 1. ተረዳዳ። 2. እርስ በርሱ፥ አንዱ ለሌላው ድጋፍ ሆነ።

ተደጋጋፊ እርስ በርስ የሚተጋገዝ፥ የሚረዳዳ።

አስደገፈ ግ ድጋፍ ላይ አደረገ፡ በድጋፍ አስያዘ።

ደጋ ስ ከባህር ወለል በጣም ከፍ ብሎ የሚገኝና የአየር ጠባዩ ቀዝቃዛ የሆነ አከባቢ፡ የቆላ ተቃራኒ።

ደገኛ ስ በደጋ የሚኖር ሰው።

ደጋሚ^1 "**ደገመ**^{1}" ስር ተመ.

ደጋሚ^2 "**ደገመ**^{2}" ስር ተመ.

ደጋሽ "**ደገሰ**" ስር ተመ.

ደጋን "**ደገነ**" ስር ተመ.

ደጋገመ "**ደገመ**^{1}" ስር ተመ.

ደጋፊ "**ደገፈ**" ስር ተመ.

ደግ ቅ 1. ጥሩ፥ መልካም። 2. ቸር፡ ለጋስ። 3.ይሁን፡ እሺ ለማለት የሚነገር አባባል።

ደገኛ ቅ ጥሩ፥ መልካም (ለነገር፡ ለሰው)።

ደግሞ "**ደገመ**^{1}" ስር ተመ.

ደግዳጋ^1 "**ደገደገ**^{1}" ስር ተመ.

ደግዳጋ^2 "**ደገደገ**^{2}" ስር ተመ.

***ደጎለጎለ**

ድጉልጉል ቅ ወፍራምና ቅርፀ ቢስ የሆነ።

ድጉልጉል አለ ግ ተድጎለጎለ።

ድጉልጉል አደረገ ግ አድጎለጎለ።

ተድጎለጎለ ግ 1. ወፍራምና ቅርፀቢስ ሆነ። 2. ከውፍረትና ከቅርፀ ቢስነት የተነሳ ቀልጣፋ ብሎ መራመድ ተሳነው።

አድጎለጎለ ግ አወፈረ፥ ቅርፀቢስ አደረገ።

ደጎመ ግ ደገፈ፥ በመጠኑ እርዳታ አደረገ፥ በጎደለ እየሞላ አገዘ (በገንዘብ፡...)።

ደጓሚ ቅ አጋዥ፡ እርዳታ የሚያደርግ (የገንዘብ፥...)።

ድጎማ ስ በጎደለ መሙያ ወይም ለማጠናከሪያ የሚሆን መጠነኛ እገዛ፡ እርዳታ (የገንዘብ፥...)።

ተደጎመ ግ ተደገፈ፡ በመጠኑ እርዳታ ተደረገለት፥ ታገዘ (በገንዘብ፥...)።

ደጎሰ ግ የመፃህፍትን ገበታ በቆዳ፥ በባህር አረብ ሸፍኖ ወይም ለብዶ ልባዱን በልዩ ልዩ ቅርፅ ሸለመ፥ አስጌጠ።

መደጎሻ ስ በመፅሃፍ ልባድ ላይ ልዩ ልዩ ቅረፆችን ለመስራት የሚያገለግል ከብረት የተሰራ

የቅርፅ ማወቂያ::

ደንሽ ስ መፅሃፍ ጠረጴዛ::

ድጉስ ስ 1. የተደጎሰ፥ የተጌጠ፡ የተሸለመ የመፅሃፍ ገበታ ሽፋን ። 2. ሰገባ፥ አፎት::

ደጎባ¹ ቅ በቂ የቀለም ትምህርት የሌለው፡ ትምህርት አልገባ የሚለው (ሰው)::

ደጎባ² ስ 1. የአንበጣ ኩብኩባ:: 2. ሰታ፥ ወባት::

ደንሚ "ደጎመ" ስር ተመ.

ደንሽ "ደጎሰ" ስር ተመ.

ደጭመረጭ ስ በቆላና በወይናደጋ አካባቢ የሚበቅልና መድሃኒትነት አለው የሚባል አነስተኛ የእፅዋት አይነት::

ደፈረ ግ 1. ጎበዘ፡ በረታ:: 2. ጨከነ፡ ሳይፈራ ቀረ:: 3. ናቀ፥ አዋረደ፥ ዝቅ አድርጎ ተመለከተ:: *እንዴት ብትደፍረኝ ነው የጎሪጥ ያየሀኝ?* 4. ሴትን በግብረ ስጋ ተገናኛ (ከፍላጎቷ ውጭ በሆነ መንገድ፡ በማስገደድ)::

ደፋር ቅ 1. ጎበዝ፡ ብርቱ፡ ቆራጥ:: 2. ጨካኝ፡ የማይፈራ:: 3. (ዘይ.) ባለጌ፥ ሰው የማያከብር::

ድፍረት ስ 1. አለመፍራት፡ ቆራጥነት:: 2. (ዘይ.) ብልግና፡ ሰው አለማክበር፥ ንቀት::

ተደፈረ ግ 1. ተጣሰ፡ ተነካ:: (ድንበር፥ ህግ፡...):: 2. (ዘይ.) ተናቀ፡ ተዋረደ::

ተደፋፈረ ግ 1. ተበረታታ፡ ሳይፈራ ቀረ:: 2.ተናናቀ::

ተደፋፈሩ (ዘይ.) በግብረ ስጋ ተዋወቁ::

ተዳፈረ ግ የድፍረት ድርጊት ፈፀመ::

አደፋፈረ ግ አበረታታ፡ አነቃቃ፡ ገፋፋ::

ደፈረሰ ግ 1. ተበጠበጠ፡ ከጭቃ፥ ከአፈር፡... ጋር ተደበላለቀ፡ ጥራቱ ተበላሸ (ውሃ):: 2. ጎሸ፥ አተላ (ጠጅ፥ ጠላ፥...):: 3. (ዘይ.) ታወከ፡ ተሸበረ፥ ተረበሸ (አገር፥ ፀጥታ፡...)::

ድፍርስ ቅ 1. ብጥብጥ፥ ከጭቃ፡ ከአፈር፡... ጋር የተደበላለቀ፥ ያልጠራ:: 2. ከአተላ ጋር የተደበላለቀ፥ ያልጠራ (ጠላ፡ ጠጅ፡...)::

አደፈረሰ ግ 1. በጠበጠ፡ ከጭቃ፡ ከአፈር፥... ጋር ደበላለቀ፡ ጥራቱን አበላሸ (የውሃን፡...):: 2.ከአተላ ጋር ደበላለቀ (ለጠላ፡ ለጠጅ፥...):: 3.አወከ፡ ረበሸ፥ አሸበረ (አገርን፡ ፀጥታን፥..)::

አደፍራሽ ቅ አዋኪ፡ በጥባጭ::

ደፈር ስ የተራራ ጫፍ፥ ገመገም::

ደፈቀ ግ ዘፈቀ፡ ነከረ (ፈሳሽ ውስጥ)::

ደፈቃ ስ 1. ዘፈቃ (በውሃ ዋና ጊዜ አንዱ ሌላውን በማስጠም የሚጫወቱት ጨዋታ:: 2. (ስፖ.) በመረብ ኳስ ጨዋታ ላይ ኳስ በተቃራኒው ቡድን ሜዳ ውስጥ እንድታርፍ አክርሮ ወደ መሬት መምታት::

ተደፈቀ ግ ተዘፈቀ፥ ተነከረ::

ደፈነ ግ 1. ክፍት የነበረውን በአንድ ነገር ዘጋ፡ ገጠመ፡ ሸፈነ፡ መረገ፥ አሸገ:: 2. ቀበረ፥ ደበቀ፡ ሰወረ:: 3. ተደፈነ (አይን):: 4. የተሰጠውን ጥያቄ ሙሉ በሙሉ መለሰ፡ ሙሉውን ነጥብ አገኘ::

በደፈናው ተቀ. በአጠቃላይ (ዝርዝር ሁኔታው ሳይገለጥ)::

ድፍን ቅ 1. ምንም ያልተነካለት፡ ሙሉ:: *ድፍን እንጀራ*:: 2. ምንም አይነት ቀዳዳ፡ ሽንቁር የሌለው:: 3. ያልተከፈተ፡ እሸግ (ውስጡ ባዶ ቦታ ሊኖረው ወይም ላይኖረው ይችላል):: 4. መላው፥ ጠቅላላው:: *ወሬውን ድፍን አዲስ አበባ ሰማው*:: 5. (ዘይ.) ከልክ በላይ ዝምታ የሚያበዛ፡ የማይናገር:: 6. ሲያናግሩት መልስ የማይሰጥ፥ ጋግርታም:: 7. (ዘይ.) ትምህርት የማይገባው::

ድፍን አለ ግ 1. በጣም ጨለመ:: 2. ዝግት አለ::

ድፍን ራስ ድንጋይ ራስ፡ ደደብ::

ድፍንፍን ቅ 1. ግልፅ ያልሆነ፡ ድፍንፍን:: 2. ልኩስኩስ፥ ርምጥምጥ፥ ስራ የማይሳካለት::

ድፍንፍን አለ ግ 1. በጣም ጨለመ:: 2. ተደፈነ::

መድፍነ ፀር ስ አንድን ሰው ጠላት እንዳይነሳበት ይረዳዋል ወይም ጠላቱ ሊያደርስበት ከሚችለው ጉዳት ሊጠብቀው ይችላል ተብሎ የሚታመንበት የአስማት አይነት::

ተደፈነ ግ 1. ክፍት የነበረው ቦታ ወይም ቀዳዳ ተዘጋ፥ ተገጠመ:: 2. ተጨፈነ (አይን በበሽታ ምክንያት)::

ተዳፈነ ግ 1. ተቀበረ፡ ተሸፈነ (እሳት፡...):: 2. (ዘይ.) በምስጢር ተያዘ፡ ተደብቆ እንዲኖር ተደረገ፥ ሳይጋለጥ ቀረ፡ ተሸፋፈነ::

ተድፈነፈነ ግ ተርመጠመጠ፥ ተልኮሰኮሰ::

አደፈነ ግ ላዩ የዳነ መስሎ ውስጡ ቂም ያዘ፡ አቀበረ፥ ለገመ (ቁስል)::

አዳፈነ ግ 1. የእሳት ፍም በአመድ ውስጥ ቀበረ፥ ሸፈነ (እንዳይጠፋ):: 2. (ዘይ.) እንዳይገለጥ ወይም ተሸፋፍኖ እንዲቀር አደረገ (አንድን ነገር ወይም ጉዳይ)::

አዳፈነበት በጥይት፥... መታው፡ ገደለው::

አድፈነፈነ ግ 1. አጭፈነፈነ:: 2. አልኮሰኮሰ፡ አርመጠመጠ:: 3. ደባበቀ::

ደፈደፈ ግ 1. እንኩሮንና ቂጣን ከጥንስስ ጋር በውሃ ለወሰ፡ አዋሃደ፥ በመፍረሻ በጠበጠ::

2. መረገ፡ ሰደፈ። *መድሃኒቱን ቁስሉ ላይ ደፈደፈ።* 3. (ዘይ.) ሳከከ፡ አሳበበ። *ጥፋቱን በሙሉ በወንድሙ ላይ ደፈደፈ።*

ድፍድፍ ስ 1. በወፍራሙ በውሃ ተለውሶ የተዘጋጀ የጥንስስ፥ የእንኩሮ፡ የቂጣ ሁሁድ፡ ድብልቅ። 2. ሳይጠራ በድፍድፍ መልክ የሚገኝ ማንኛውም ጥንተ ነገር። *የነዳጅ ዘይት ድፍድፍ።*

ድፍድፍ አለ ግ ወፈረ (ለቅርፅ)።

***ደፈደፈ**

ደፈደፍ (ደፈዳፋ) ቅ ርብትብት።

ደፍደፍ አለ ግ ተንደፈደፈ።

ተንደፋደፈ ግ 1.ተንፈራፈረ፥ ተንፈራገጠ። 2. ተፍጨረጨረ፡ ተግጠረ። 3. ተርመጠመጠ፥ ተልከሰከሰ።

አንደፋደፈ ግ 1. አንፈራፈረ፥ አንፈራገጠ። 2. አርመጠመጠ።

ደፈጠ ግ 1 ሸመቀ፡ ተደበቀ። 2. አጠመደ።

ደፈጣ ስ ሸመቃ።

የደፈጣ ውጊያ ስ ሽምቅ ውጊያ።

ደፋጣ ቅ ሰዋራ፡ ደባቃ (ቦታ)።

አደፈጠ ግ አሸመቀ፥ ተደበቀ።

አድፋጭ ቅ 1. ሸማቂ። 2. (ዘይ.) ሁኔታዎች እስከሚረጋጉ ወይም እስከሚለይላቸው ድረስ ድምፁን አጥፍቶ የሚቀመጥ።

ደፈጠጠ (ደፈጨጨ) ግ ረገጠ፡ ጸመጠ፡ ጨፈለቀ፡ ጸጠ።

ደፍጣጣ(ድፍጥጥ፥ ድፍጥ) ቅ 1. ቅርፁ የተበላሸ፡ የተጠፈጠፈ። 2.አፍንጫው ጠፍጣፋ የሆነ።

ተደፈጠጠ ግ 1. ተረገጠ፡ ተጸመጠ፡ ተጨፈለቀ፡ተጸጠ። 2. ተጠፈጠፈ፥ ደፍጣጣ ሆነ።

***ደፈጠፈጠ**

ድፍጥፍጥ አለ ግ ተድፈጠፈጠ።

ድፍጥፍጥ አደረገ ግ አድፈጠፈጠ።

ተድፈጠፈጠ ግ ተፍረጠረጠ።

አድፈጠፈጠ ግ አፍረጠረጠ።

ደፈጣ " **ደፈጠ**" ስር ተመ.

ደፈጨጨ "**ደፈጠጠ**" ን ተመ.

ደፈጫ ስ እብ ።

ደፋ ግ 1. ባፍጢሙ ጣለ፡ ፈነገለ። 2. አፈሰሰ፡ ከነበለ (ፈሳሽን)። 3. ዘረገፈ፥ ገለበጠ (ፈሳሽ ያልሆነን ነገር)። 4. አዘነበለ፡ ወደ አንድ በኩል አመዘነ። 5. አፉን ወደ መሬት አድርጎ አስቀመጠ (እቃን)። 6. በአደራ አስቀመጠ (ሳይሸጥ የቀረን እቃ)።

ደፋት ያለ ውዴታዋ በግብረ ስጋ ተገናኛት።

ደፋው ገደለው።

ደፋ ቀና አለ ግ በስራ ተጠመደ፡ ለፋ፡ ባተሌ ሆነ።

ደፋታ ስ ቁልቁለት፡ ሽርታታ።

ድፋት ስ የድምፅ ዜማ ምልክት፡ ምልክቱም (∩) ነው።

ድፈት ስ በቆብ ቅርፅ የሚሰራ የሹርባ አይነት።

ድፎ ስ የአበሻ ትልቅ ዳቦ።

ደፋፋ ግ 1. አፋሰሰ። 2. አባከነ። 3. በርካሽ ቶሎ ቶሎ ሸጠ።

ደፋ ደፋ አለ ግ በመቻኮል ቶሎ ቶሎ ሄደ።

ደፋ ደፋ አደረገ ግ ደፋፋ፡ ቶሎ ቶሎ ፈጸመ፡ አደረገ።

ድፍት ብሎ ቀረ ሞተ (ብዙውን ጊዜ ባልታሰበ ቀንና ቦታ)።

ድፍት ብሎ አደረ ጦሙን አደረ።

ተደፋ ግ 1. ተፈነገለ፥ ወደቀ። 2. ፈሰሰ፥ ተከነበለ። 3. አዘነበለ (ወደ አንድ በኩል)።

ተደፋፋ ግ ተድፋፋ።

ተዳፋ ግ ተቆለቆለ፥ ወደታች ወረደ።

ተዳፋት ስ ቁልቁለት።

ተድፋፋ ግ ባከነ፡ ያለ አግባብ ቶሎ ቶሎ እንዲያልቅ ሆነ።

አዳፋ ግ ገፈተረ፡ አንገላታ፡ አጣደፈ፡ አቻኮለ።

አድፋፋ ግ አባከነ፡ ያለ አግባብ እንዲያልቅ አደረገ።

አድፋፊ ቅ አባካኝ።

ደፋር " **ደፈረ**" ስር ተመ.

ደፋታ "**ደፋ**" ስር ተመ.

ደፋጣ "**ደፈጠ**" ስር ተመ.

ደፋፋ "**ደፋ**" ስር ተመ.

ደፍ ስ የግራና የቀኝ መቃኖችን የሚያቆሙበት ከመዝጊያ ስር የሚገኝ አግዳሚ እንጨት(ቤት ስር የ"**በር**"ን ስእል ተመ.)።

ደፍ ደፍ አለ "***ደፈደፈ**" ስር ተመ.

ደፍዳፋ "***ደፈደፈ**" ስር "**ደፈደፍ**"ን ተመ.

ደፍጣጣ "***ደፈጠጠ**" ስር ተመ.

ዱ የ "**ደ**" ፊደል ካእብ ዘር።

ዱለታ "**ዶለተ**" ስር ተመ.

ዱለት^{1} ስ ከተከተፈ የበግ ወይም የፍየል ጨጓራና ጉበት በድልህና በቅቤ የሚዘጋጅ ምግብ (እንደአስፈላጊነቱ አንዳንድ ጊዜ የሸንጥ ስጋ

በመጠኑ ይታከልበታል)።

ዱለት^2 "ዶለተ" ስር "ዱለታ"ን ተመ.

ዱላ ስ 1. ለማምቻ፣ ለመመርኰዣ፣... እንዲያገለግል ሆኖ ከእንጨት የሚዘጋጅ በትር። 2. (ዘይ.) ድብድብ፣ ጠብ።

በዱላ ተለቀቀበት (ተለቀቀው) በዱላ ደበደበው።

በዱላ አንቆራጠጠ እየተከታተለ በዱላ መታ፣ ነረተ፣ ደበደበ።

በዱላ ከካው ጭንቅላቱን በዱላ ፈነከተው።

ዱላ ቀረሽ ጠብ ስ ከዱላ በመለስ በቃላት ወይም በስድብ ብቻ የሚካሄድ ከፍተኛ ጠብ።

ዱለኛ ቅ ተደባዳቢ።

ዱልዱም "ዶለዶመ" ስር ተመ.

ዱማች ስ ምሳ፣ የቀንኛ።

ዱር ስ ጫካ፣ ደን፣ ሰው ያልሰፈረበት ቦታ።

ዱር ቤቴ አለ ወመኔ ሆነ፣ እቤቱ ማደር ተወ፣ ወነበደ፣ ሸፈተ።

ዱር አደሬ ቅ 1. ቤት የለሽ። 2. ዱርዬ።

ዱርዬ ቅ ወመኔ።

ዱርር "*ዶረረ" ስር ተመ.

ዱርሸት ስ ቅጠሉ የሚከረፋ፣ የሚገማ የሃረግ አይነት።

ዱርዬ "ዱር" ስር ተመ.

ዱሮ(ድሮ) ስ 1. ጥንት፣ ቀድሞ የነበረው ጊዜ። *በድሮ በሬ ያረሰ የለም*፡ ተው.ግ. 2. ከዚህ ፊት በነበረው ጊዜ። *ድሮ የገዛው ልብስ አለ።*

ዱሽ ስ 1. ኩንትሽ፣ ጣቶቹ የተቆረጡ እጅ ወይም እግር። 2. ቆማጣ።

ዱቄት ስ የደቀቀ፣ የተፈጨ፣ የላመ (ብዙውን ጊዜ እህል)።

ዱቄት ሆነ በጣም ደቀቀ፣ ተሰባበረ።

ዱቅንዱቅ (ዱቀንዱቂት) ስ የትል አይነት።

ዱቢት ስ 1. ወፍራም የሽንብራ እንጀራ፣ ሰረባት። 2. በአሳ አምሳያ ከሽንብራ የሚዘጋጅ ትንሽ ጥቢኛ።

ዱባ ስ 1. ተቀቅሎ የሚበላ ድቡልቡል ወይም ሞላላ የሆነ ትልቅ ፍሬ ያለው ሃረግማ ተክል፤ ፍሬውም ዱባ ይባላል። 2. (ዘይ.) አጭርና ወፍራም የሆነ (ሰው)።



ዱባ 1ኛ ፍቺ

[የ] ዱባ ፍሬ ስ ነጭና ጠፍጣፋ የሆነ የዱባ ተክል ዘር።

ዱቤ ስ የእቃውን ወይም የአገልግሎቱን ዋጋ በሌላ ጊዜ ለሚከፈል፣ በገዥና በሻጭ መካከል የሚካሄድ የገበያ ስምምነት።

ዱቬ ስ በፋብሪካ ተዘጋጅቶ የሚቀርብ የዱቄት አይነት።

ዱቬ በርበሬ ስ ዛላው ወፍራምና ረዥምም የሆነ የማይፋጅ በርበሬ።

ዱብ

ዱብ እዳ ስ ድንገተኛ፣ ያልታሰበና ያልተፈለገ ነገር። *የመሬትና የትርፍ ቤት መወረስ ለቆጆ ዱብ እዳ ነበር የሆነባቸው።*

ዱብ አለ ግ 1. ከላይ ወደታች ዘለለ፣ ጡብ አለ። 2. ወደቀ፣ ጠብ አለ (ዝናብ፣ እንባ)።

ዱብ አደረገ ግ ጣለ።

ዱብ ዱብ አለ ግ 1. አንድ ቦታ ላይ ሆኖ ደጋግሞ ዘለለ፤ እንጣጥ እንጣጥ አለ። 2. ጠብ ጠብ አለ፣ ወዳደቀ።

ዱብ ዱብ አደረገ ግ 1. ጠብጠብ አደረገ፣ አፈሰሰ (እንባን፣ ዝናብን፣...)። 2. ጣል ጣል አደረገ፣ አንጠባጠበ።

ዱታ

ዱታ ነኝ አለ ያዙኝ ልቀቁኝ አለ፣ ለመማታት፣... ተጋበዘ።

ዱካ^1 "ደከ^1" ስር ተመ.

ዱካ^2 ስ በርጩማ፣ ግርንቡድ።

ዱያታም "ደዌ" ስር ተመ.

ዱያት "ደዌ"ን ተመ.

ዱዳ(ዲዳ) ቅ 1. መናገር የማይችል (ሰው)። 2. (ዘይ.) ሃሳቡን ወይም የልቡን አውጥቶ፣ አብራርቶ፣ ግልፅ አድርጎ መናገር የማይችል።

ዱድማ ዝ.ከ.

ዱግ ስ 1. ቀደም ባለው ጊዜ የሹም ወኪል ወይም እንደራሴ መጠሪያ። 2. ተወዳጅ፣ ዝቅተኛ፣ የበታች ሹም።

ዴ የ "ደ" ፊደል ሳልስ ዘር።

ዴሞትፈር ስ የጠመንጃ አይነት።

ዲሞክራሲ ስ 1. ስልጣን በጠቅላላው ህዝብ በሚመረጡ ተወካዮች እጅ የሚሆንበት ስርአተመንግስት። 2. የተለያዩ ፖለቲካዊ አመለካከቶችን፣ የንግግር፣ የፅሁፍ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ፣... ነፃነትን የሚፈቅድ ስርአት።

ዲሞክራሲያዊ ቅ ህዝባዊ።

ዲሞክራት ስ አፍቃሪ ዲሞክራሲ የሆነ ሰው።

ዲሬክተር(ዳይሬክተር) ስ 1. የትምህርት

ቤት ስራ መሪ፤ ርእሰ መምህር። 2. ስራ አስኪያጅ፤ ስራ መሪ።

ዴር ስ 1. ጥሩር፥ ከብረት የተሰራ ልብስ። 2. የድንጋይ አጥር። 3. በሰንበረዥ መጫወቻ ውስጥ ያለ ግንብ። 4. ፈረሰኛ።

ዲስክስ(ዲስክ) ስ ከድንጋይ፥ ከእንጨት ወይም ከብረት የሚሰራ፤ ቅርፁ ክብና ጠፍጣፋ የሆነ፥ ለውርወራ ስፖርት የሚያገለግል እቃ።

ዲስኩር ስ ብዙ ሰው በተሰበሰበበት የሚደረግ ንግግር።

ዲቃላ "ደቀለ" ስር ተመ.

ዲባታማ ስ መልኩ ወደዳለቻነት የሚያደላና ፈካ ያለ ወይን ጠጅ የሚመስል፥ እንደ ማጭድ ወደፊት የጎበጡ ቀንዶች ያሉት፤ በበረሃማ ስፍራዎች የሚገኝ፥ አንገተ ረጅም የሆነ፥ እፅዋት በል እንስሳ ።

ዲብ ስ ከፍታው አነስተኛ የሆነ የአፈር ጉብታ፥ ቁልልታ።

ዲና ስ አመፀኛ፥ አደጋ ጣይ (ሰው)።

ዲና ደመታ አደጋ ጣለ።

ዲናሞ ስ የእንፋሎትን ወይም የውሃን፥...ሃይል ወደ ኤሌክትሪክ ሃይል የሚለውጥ ሜካኒካዊ መሳሪያ።

ዲናር ስ የገንዘብ ስም።

ዲዛይን ስ አንድ ነገር በተጨባጭ ከመሰራቱ በፊት በወረቀት ላይ ተስሎ የሚታይ ንድፍ።

ዲያቆን "ዳቆን" ስር ተመ.

ዲያቢሎስ(ዲያብሎስ) ስ 1. የሰይጣን አለቃ። 2. (ዘይ.) ርጉም፥ ክፉ።

ዲደን ስ ብርዳማ የሆነ ሃይለኛ ነፋስ።

ዲዳ "ዱዳ" ን ተመ.

ዲግሪ ስ 1. በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ትምህርቱን ተከታትሎ ለፈፀመና ፈተናውን ላለፈ ሰው የሚሰጥ የምስክር ወረቀት፤ የትምህርት ማስረጃ። 2. የማእዘን ወይም ዘዌ መለኪያ አሃድ። 3. የሙቀት መጠን መለኪያ አሃድ። *በመቶ ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ ውሃ ወደ እንፋሎትነት ይለወጣል።*

የዲግሪ ፕሮግራም [ትምህርት] ስ የአስራ ሁለተኛ ክፍልን ብሄራዊ ፈተና ካለፉ በኋላ በዩኒቨርስቲ ውስጥ በተለያዩ የትምህርት ዘርፎች ለአራት አመት ወይም ከዚያ በላይ የሚሰጥ የትምህርት ፕሮግራም።

ዲፕሎማ (ዲፕሎም) ስ በተወሰነ የትምህርት ዘርፍ ላይ ተገቢውን ስልጠና ወይም እውቀት ላገኘ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ወይም የትምህርት ማስረጃ።

ዲፕሎማሲ ስ በሃገሮች መካከል ሊኖር የሚገባውን ግንኙነት አስመልክቶ በየውጪ ጉዳይ መስሪያ ቤቶች በኩል በተመደቡ የኤምባሲ ሰራተኞች የሚከናወን ስራ፤ ከላይ የተጠቀሰውን ስራ የማከናወን ዘዴ፥ ጥበብ።

ዲፕሎማት ስ የዲፕሎማሲን ስራ የሚያከናውን ግለሰብ፤ የኤምባሲ ከፍተኛ ባለስልጣን።

ዲፕሎም "ዲፕሎማ" ን ተመ.

ዳ የ "ደ" ፊደል ራብእ ዘር።

ዳሀ(ዳኸ) ግ በእግርና በእጁ ሄደ (በተለይ ለህፃን)።

ዳህራይ "ደሃራይ" ን ተመ.

ዳለቻ(ዳለቸ) ቅ አመድማ፤ ቡላ፥ ግራጫ ቀለም ያለው።

ዳለጠ ግ ሟለጠ።

ዳላጣ ቅ ድጥ፥ የሚያሟልጥ።

አዳለጠ ግ አሟለጠ፥ አዳጠ፥ አሟለጨ።

ዳሌ ስ ከጭን በላይ፥ ከወገብ በታች ያለ የሰውነት ክፍል።

ዳሊጋ ስ በበሬ፤ በላም፥... አንገት ላይ ከማንቁርት እስከ ፍርንባ የተንጠለጠለ ቆዳ።

[የ] ዳሊጋ አንበሳ ስ አሸዋማ ቀይ ሆኖ ወደ ሆዱ ነጣ የሚልና ወደ ጉያውና እግሮቹ አካባቢ ደብዘዝ ያሉ ጠቃጠቆ ምልክቶች ያሉበት፥ የኋላ እግሮቹ ከፊተኛቹ ይበልጥ ረዘም የሚሉ፥ ታላላቅ ቋጥኞች በሚገኙባቸው ኮረብታዎች ላይ የሚኖር፥ የአንበሳ ዘር የሆነ የዱር አውሬ (በእሱን የዱር\እንስሳ ስር ተመ.)።

ዳመነ ግ ደመና ሆነ።

ዳመና(ደመና) ስ በእንፋሎት ወይም በተን መልክ ከመሬት ከተነሳ በኋላ የተንደፈ ጥጥ በመምሰልና ልዩ ልዩ ቅርፅ በመያዝ በሰማይ ላይ ሲንሳፈፍ የሚታይ ረቂቅ የሆኑ የውሃ ነጠብጣብ ክምችት።

ዳመና አረገዘ(ጣለ) ዳመና አንገረበበ፥ ዳመና ሆነ፤ ሊዘንብ የተቃረበ መሰለ።

ድምንምን አለ ግ ጥቁርቁር፥ ጭልምልም አለ።

ተድመነመነ ግ ጠቋቆረ፤ ጭልምልም አለ።

አዳመነ ግ ዳመነ።

አድመነመነ ግ አጠቋቆረ፥ አጨላለመ።

ዳመጠ ግ 1. ዳጠ፤ ደፈጠጠ። 2. አብጣ ጎብጣ የነበረውን እንዲስተካከል ወይም ልስቅ እንዲል አደረገ። 3. የተፈለቀቀን ጥጥ በመዳመጫ ድንጋይ ላይ በማድረግና እጥርና ቀጭን በሆነ የብረት ዘንግ ከላይ ወደታች በመዳጥ ጥጡን ከፍሬው ለየ።

መዳመጫ ስ ጥጥን ለመዳመጥ የሚያገለግል ጠፍጣፋና ለስላሳ ድንጋይ።

የመዳመጫ ብረት ስ የተፈለቀቀን ጥጥ ከፍሬው ለመለየት የሚያገለግል አጭር፡ ቀጭንና ለስላሳ የሆነ የብረት ዘንግ።

ዳሙጠ ስ 1. በመዳመጫ ተዳምጦ ከፍሬው የተለየ ጥጥ። 2 (ዘይ.) ኣፍንጫ ደፍጣጣ (ሰው)።

ዳማ^{1} ቅ ደም የሚመስል የቀይ አይነት። *ዳማ ፈረስ።*

ዳማ^{2} ስ ክብና ጠፍጣፋ ሆነው ከፕላስቲክ ወይም ከእንጨት፡... የተሰሩ ጠጠሮችን በሰሌዳ ላይ በማንቀሳቀስ የሚደረግ ጨዋታ።

ዳማከሴ ስ ሰዎች ለመድሃኒትነት የሚጠቀሙበት የእፅዋት አይነት።

ዳምጠው ስ መንገድ ሲሰራ በትላልቅ የብረት መዳመጫዎች ንጣፉን እየዳመጠ የሚያስተካክል እጅግ ከባድ ተሽከርካሪ።

ዳሞትራ ስ መልኳ ሸረሪት የሚመስል ጥቁርና ተናዳፊ የሆነች ነፍሳት።

ዳሞት ወይራ ስ እንደ ወይራ ጠንካራ የሆነ የዛፍ አይነት።

ዳረ ግ አጋባ፥ ትዳር ኣስያዘ፡ ሴትና ወንድን በትዳር ኣጣመረ፥ ጋብቻ እንዲመሰርቱ አደረገ።

መዳሪያ ስ ልጆች በተጋቡ ጊዜ ከወላጆች የሚሰጥ ሃብት፥ ንብረት።

ዳረገ ግ 1. ድርጎ ፈቀደ፡ እንዲሰጥ አደረገ። 2. (ዘይ.) አጋለጠ፥ አሳልፎ ሰጠ።

ዳረጎት ስ 1. ድርጎ። 2. ስጦታ፥ ጉርሻ።

ድርጎ ስ 1. በተወሰነ ጊዜ ለድርጎኛ የሚሰጥ የተወሰነ መጠን ያለው ምግብ፥ መጠጥ፡...። 2. እንደ እርቦ ያለ መስፈሪያ፥ መለኪያ።

ድርጎኛ ቅ በተወሰነ ጊዜ የተወሰነ መጠን ያለው ምግብና መጠጥ፥... የሚሰጠው ወይም የሚቀበል ሰው።

ተዳረገ ግ 1. ተሰጠ። 2. ለችግር፥ ለመከራ፡... ተጋለጠ።

አደራጎተ ግ ዳረጎት ሰጠ።

ዳሩ ታዲያ፥ ግን። *ፈልጌው ነበር፤ ዳሩ ምን ያደርጋል ላገኘሁትም፡*

ዳሩ ግን የሆነ ሆኖ፥ ግን፥ ሆኖም፡ ምን ያደርጋል፥ ምን ይሆናል። *ትምህርቱን ተከታትዬ ነበር፤ ዳሩ ግን ፈተናውን ኣልወሰድኩም፡*

ዳራ "ደሃራይ" ን ተመ.

ዳር (ዳርቻ) ስ 1. ጠርዝ፡ ጫፍ። 2. አጠገብ። *ቤቱ ከመንገድ ዳር ነው።* 3. ከአንድ ከተወሰነ ክልል ውጭ። *ዳሩ ወደዳር ወጣች፡* 4. መጨረሻ፥ ጫፍ። *ነገሩ ዳር ሳይደርስ ኣልቀረም፡*

ዳር ኣገር ጠረፍ። *ለውጊያው ዳር ኣገር ይኖራል።*

ዳር ኣደረሰ ፍፃሜ አደረሰ።

ዳር ወጣ 1. ይፋ ሆነ። *ነገሩ ዳር ወጣ፡* 2. ሊያልቅ ደረሰ። *ነገሩ ዳር ደርሷል።*

ዳር ዳር ኣለ 1. ከጀለ። 2. ኣመነታ። *መወሰን ኣቅቶት ዳር ዳር ይላል።*

ዳር እስከ ዳር በሙሉ፥ በጠቅላላው። *ወሬውን ሀገሩ ዳር እስከ ዳር ሰምቶታል።*

ዳሰ ግ 1. የወፍጮውን መጅ በሃይል ሳይጫን ወይም ሳያጠብቅ እንደ ኣሻሮ ያለውን እህል በቀላሉ ፈጨት ፈጨት አደረገ። 2. ዳመጠ፡ ደፈጠጠ።

መዳሻ ስ ትልቅ የወፍጮ መጅ።

ዳሰሰ ግ 1. ዳበሰ፥ ነካ፥ ነካካ። 2. ቃኘ፥ ፈለገ።

ዳሰሳ ስ 1. ዳበሳ፡ መነካካት። 2. ኣንድን ጉዳይ በተመለከተ የሚደረግ ቅኝት ወይም ኣጠቃላይ የሆነ ፍለጋ ወይም የግኝቱ ገለፃ።

በዳሰሳ በግምት፥ በመላ።

ዳስ ስ ብዙውን ጊዜ ድግስ ያለባቸው የገጠር ሰዎች እንግዶቻቸውን በአንድነት ለማጋበዝ ያስችላቸው ዘንድ እንደ ኣጠና፡ ጨፈቃና ቅጠላ ቅጠል ባሉ ነገሮች የሚሰሩት ጊዜያዊ መጠለያ።

ዳስ ጣለ ዳስ ሰራ፥ አዘጋጀ።

ዳስተር ስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በጠመኔ የተፃፈን ፅሁፍ ለመጥረግ፡ ለማጥፋት የሚያገለግል ፀጉራም መጥረጊያ።

ዳሸቀ ግ 1. ተረገጠ፥ ታሸ፥ ደቀቀ። 2. በሰበሰ፥ በካ (ጭቃ)። 3. ደከመ፡ አቅም የሌለው ሆነ። *ኢኮኖሚው ዳሽቋል።*

አዳሸቀ ግ በሃይል መታ፥ ረገጠ።

ዳቆነ ግ የድቁና ማእረግ ተቀበለ።

ድቁና ስ የዲያቆንነት ማእረግ፡ ስልጣን።

ዲያቆን ስ በድቁና ማእረግ በቤተክርስቲያን የሚያገለግል ቀዳሽ፡ ካህን።

አዳቆነ ግ የዲያቆንነት ማእረግ ወይም ስልጣን ሰጠ።

ዳበረ ግ 1. ፋፋ፥ ወፈረ፥ ተመቸው። 2. ሰፋ፡ ተስፋፋ፥ ብዛት አገኘ። 3. ለተክል፡ ለሰብል የሚስማማና የሚጠቅም ጥሩ አፈር ሆነ። 4. አደገ፡ ላቀ፥ ጨመረ።

አዳበረ ግ አሳደገ፥ ቀደም ሲል በነበረው ላይ በመጨመር አስፋፋ (ለምሳሌ ሃሳብን)።

ማዳበሪያ ስ አፈር ለተክል ወይም ለሰብል ተስማሚና ጠቃሚ ነገር እንዲኖረው የሚያደርግ እንደ ፍግ ያለ ወይም በፋብሪካ ተሰርቶ የሚወጣ የልዩ ልዩ ንጥረነገሮች ውሁድ።

አዳባሪ ሃሳብ ስ አጎላማሽ፡ አጠናካሪ ሃሳብ።

ዳበሰ ግ 1. ነካካ፥ ዳሰሰ። 2. ፈተሸ፥ መረመረ፡

ፈለገ (በእጅ በመነካካት)።

ዳበሳ ስ ዳሰሳ።

በዳበሳ 1. ማየት በማይቻልበት ሁኔታ በእጅ ብቻ በመነካካትና በመረዳት። *ክበሪቱን በዳበሳ አገኘሁት*። 2. በግምት፣ በመላ፣ በዳሰሳ።

ዳቢት ስ የጎድን ዘርፍ፣ ከብራኳ ጋር የተያያዘ የትከሻ ስጋ።

ዳባ ስ 1. የበሬ ቆዳ፣ ቁርበት። 2. ከበሬ፣ ከኢጋዘን፣...ቆዳ የሚሰራ የመናንያን ልብስ፣ ኣፅፍ።

ዳባ ለባሽ ስ የበሬ፣ የኢጋዘን፣... ቆዳ የሚለብስ መናኝ መነኩሲ።

ዳቤ ስ ሊጡ በወፍራሙ ተዘጋጅቶ የሚጋገር ወፍራም እንጀራ።

ዳብሬ ስ ከእንስራ ኣነስ የሚል ትልቅ ገንቦ።

ዳቦ ስ 1. ብዙውን ጊዜ የስንዴ ዱቄት በወፍራሙ ተቦክቶ በተለያየ ቅርፅና መጠን የሚዘጋጅ ምግብ። 2. (ዘይ.) ወፍራም (እንጀራ ወይም መጠጥ)።

ዳቦ ደፋ ዳቦ (ድፎ) ጋገረ፣

ዳቦ ቆሎ ስ በኣብዛኛው የስንዴ ወይም የፍርኖ ዱቄት በወፍራሙ ከተቦካ በኋላ ሊጡ እየተድበለበለ በቆሎ ቅርፅ ተዘጋጅቶና ተቆልቶ የሚቀርብ የምግብ አይነት።

ዳቦት ስ ቻቦ።

ዳተኛ ቅ ቸልተኛ፣ ልግመኛ።

ዳነ ግ 1. ህመሙ ለቀቀው፣ ተፈወሰ፣ ታሞ የነበረው ጤነኛ ሆነ፣ ሻረ። 2. ተረፈ፣ አመለጠ። *ደርቦ ከለበሰው ኣደጋ እርሱ ብቻ ዳነ*።

መዳኛ ስ 1. መትረፊያ፣ ማምለጫ። *መዳኛ የለውም*። 2. መድሃኒት።

መድሃኒት(መዳኒት) ስ 1. ከተለያዩ ስራስሮች፣ ማእድናት ቅጠላ ቅጠሎች፣... በዱቄት፣ በእንክብል፣ በቅባት፣ በፈሳሽ፣... መልክ የሚዘጋጅ የህመም መፈወሻ። 2. ኣብነት። 3. በጤና ላይ ጉዳት የሚያስከትል መተት፣ ድግምት፣ ስራይ፣...።

መድሃኒት ቀመሰ 1. የነሶ መድሃኒት ጠጣ። 2. በጠላት የተዘጋጀ ጎጂ መድሃኒት ተደረገበት (በምግብ ወይም በመጠጥ አማካይነት)።

መድሃኒት ነክቶታል መጥፎ መተት፣ መድሃኒት ተደርጎበታል ።

መድሃኒት ቀማሚ የተለያዩ መድሃኒቶችን በተለያየ መልክ የሚያዘጋጅ ባለሙያ ።

መድሃኒት ቤት ስ መድሃኒት የሚሸጥበት መደብር ።

መድሃኒተኛ ስ 1. ባለመድሃኒት፣ መድሃኒት ኣዋቂ። 2. ጠላቶቹ ናቸው ብሎ በሚገምታቸው ሰዎች ላይ ጎጂ መድሃኒት የሚያደርግ ሰው ።

መድን(መድህን) ስ ዋቢ፣ ዋስትና ።

ተዳነ ግ ዋቢ፣ መድን ሆነ። *ማን ተዳነህ* ።

ኣዳኝ ቅ ፈዋሽ ።

ዳንስ "ደነሰ" ስር ተመ.

ዳንኪራ ስ 1. ጭፈራ፣ ድለቃ፣ ዝላይ። 2. ሽብሸባ፣

ዳንኪራ መታ /ረገጠ ጨፈረ፣ ደለቀ።

ዳንዳ "ደንዳ" ን ተመ.

ዳንዴ ቅ 1. ጠረንገሉ፣ ጠብደል። 2. (ዘይ.) ወንበዴ፣ ቀማኛ ።

ዳንግሌ በግ ስ ቅላቱ እሳት የሚመስል ቀይ በግ።

ዳኘ ግ የከሳሽንና የተከሳሽን፣ የበዳይንና የተበዳይን ክርክር ወይም ጉዳይ ሰምቶ ፍርድ ሰጠ።

ዳኛ ስ 1. ኣንድን ጉዳይ ኣስመልክቶ ብያኔ፣ ፍርድ፣ ውሳኔ፣...ለመስጠት ስልጣን ያለው ሰው። 2. (ስፖ.) በአንድ ስፖርታዊ ውድድር ወቅት እንደ ውድድሩ አይነት ከሜዳው ውጭ ወይም ከሜዳው ውስጥ በመሆን የስፖርት ህጎች መከበርን የሚቆጣጠርና ውሳኔ የሚሰጥ።

ዳኛ ረገጠ አልዳኝም አለ፣ የዳኛን ፍርድ ኣንኳሰሰ ።

ዳኛ ቀጠነኝ አለ ዳኛን ናቀ ።

የዳኛ ራት ስ ወደ ኣንድ አካባቢ ለሄደ ባለስልጣን የአካባቢው ነዋሪ ኣዋጥቶ ያቀረበው የነበረ ምግብና መጠጥ ።

ዳኝነት ስ የመፍረድ፣ የመወሰን፣ የመበየን ተግባር ።

ዳኝነት ገባ 1. የተወሰነበትን የዳኝነት መቀጫ ከፈለ። 2. የዳኝነት መቀጫ ተጣለበት ።

የዳኝነት የዳኝነቱን ስራ ላከናወነው ፍርድ ቤት ተረቺው የሚከፍለው ገንዘብ ።

ተዳኘ ግ ለህግ ቀረበ፣ ታዘዘ፣ የዳኛን ብያኔ ተቀበለ፣ ስርኣት ያዘ ።

ኣዳኘ ግ ለዳኛ አቤት ኣለ፣ ከሰሰ ።

ዳከረ ግ 1. ላቆጠ፣ ተለወሰ። (ጭቃ ውስጥ)። 2. (ዘይ.) በጣም ለፋ፣ ደከመ፣ ማሰነ ።

ኣዳከረ ግ 1. ኣላቆጠ፣ ለወሰ። 2. በጣም አለፋ፣ አማሰነ ።

ኣዳካሪ ቅ በማይመለከተው ጉዳይ ውስጥ ጥልቅ የሚል፣ ዘባራቂ፣ የሰው ጉዳይ የሚያበላሽ ።

ዳካ ስ ብዙውን ጊዜ ለማቡኪያ የሚያገለግል እንደ ዋዲያት ያለ እቃ ::

ዳክዬ ስ የእግሮቹ ጣቶች እርስ በርሳቸው በስስ ቆዳ የተያያዙ፥ ምንቃሩ ጠፍጣፋ የሚል፥ አንገቱና እራሱ ላይ የሚያብለጨልጭ ግራጫ ቀለም ያለው፥ በወንዝ፥ በባህር ወይም በየብስ የሚኖር የአሞራ አይነት(ስእሉን አሞራ ስር ተመ.)::

ዳዊት(መዝሙረ ዳዊት) ስ በመፅሃፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኝ የፀሎት መፅሃፍ ክፍል ወይም ራሱን ችሉ የተዘጋጀ የዚሁ የፀሎት መፅሃፍ መጠሪያ::

ዳዊት ደገመ 1. መፅሃፈ ዳዊትን ተምሮ ጨረሰ:: 2. መፅሃፈ ዳዊትን በማንበብ ፀለየ፥ፀሎት አደረገ ::

ዳዊት ደጋሚ ስ 1. ፀሎተኛ(ዳዊትን በማንበብ):: 2. ከዳዊት ትምህርት በስተቀር ተጨማሪ ሌላ ትምህርት የሌለው::

ዳዊት አስደገመ 1. ዳዊት ተምሮ እንዲጨርስ አደረገ:: 2. የዳዊት ፀሎት እንዲፀለይለት አደረገ::

ዳዋ ስ ጥሻ::

ዳውላ ስ 1. ሃያ ቁና የሚይዝ ትልቅ ስልቻ:: 2. በጭነት ከብት ጀርባ ላይ የሚደረግ መደላድል፥ የቁርቋሬ መከላከያ:: 3. (ዘይ.፥ ስድብ) ጠብደል::

ዳውጃ ስ ከቄጤማና ከቃጫ የሚሰራ ምንጣፍ::

ዳዳ ግ ከጀለ፥ማድረግ ፈለገ::

ዳዴ ስ ህፃን ልጅ በሌላ ሰው እየተደገፈ የሚያደርገው የመራመድ ልምምድ ወይም ሙከራ::

ዳዴ አለ ግ 1. ለመራመድ ሞከረ (ህፃን):: 2. ቀስ እያለ ሄደ:: 3. እድገቱ ፍጥነት በሌለው ሁኔታ ሆነ::

***ዳገተ**

ዳገት ስ አቀበት፥ ወደፊት ሲሄዱ ከፍ እያለ የሚሄድ አስቸጋሪ መንገድ ወይም ቦታ፥ የቁልቁለት ተቃራኒ::

አዳገተ ግ አስቸገረ፥ አቃተ::

አዳጋች ቅ አስቸጋሪ፥አዋኪ::

ዳጉሳ ስ ፍሬው ጥቁር፥ቀይ ወይም ነጭ የሆነና ጎመን ዘር የሚያክል የእህል አይነት::

ዳግመኛ "**ደገመ**^{1}" ስር ተመ.

ዳግሚያ "**ደገመ**^{1}" ስር "**ዳግም**" ን ተመ.

ዳግማዊ "**ደገመ**^{1}" ስር ተመ.

ዳግም ገ.ከ.

ዳግሞሽ "**ደገመ**^{1}" ስር "**ዳግመኛ**" ን ተመ.

ዳኅሰ ግ ወፈረ::

ዳኅስ ያለ ቅ ወፈር ያለ::

ዳጠ ግ 1. ደፈጠጠ፥ጨፈለቀ:: 2. ዳለጠ፥ ድጥ ሆነ፥ እግር አስከዳ፥ አንሸተተ::

ዳጥ ስ ሲረግጡት የሚያሟልጭ ጭቃማ (ቦታ)::

ድጥ ገ.ከ.

ድጣም ቅ ዳጥ የሆነ (ቦታ)::

አዳጠ ግ አዳለጠ፥አንሸራተተ::

ዳፈ ግ ገፋ፥ አዳፋ፥ገፈተረ::

ዳፈሰ ግ ጎፍላ አይነት ፀጉር አወጣ፥ፀጉራም ሆነ::

***ዳፈነ**

ዳፈን ስ 1. አንድን ግዴታ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ያለመፈፀም ሁኔታ (ግብርን በወቅቱ አለመክፈል፥ቅጣቱን ማስታጎል፥...):: 2. አንድን ግዴታ በተወሰነ ጊዜ ባለመፈፀም ምክንያት የሚከፈል መቀጮ::

ተዳፈነ ግ 1. ታጎለ፥ መፈፀም የነበረበት ነገር ሳይፈፀም ቀረ:: 2. አመድ ለበሰ፥ ተቀበረ(እሳት)::

አዳፈነ ግ አስታጎለ፥መፈፀም የሚገባውን ነገር ሳይፈፀም ቀረ::

ዳፋ ስ ጦስ፥መዘዝ::

ዳፍንት ስ እነስተኛ ብርሃን ባለበት ወይም በጨለማ ውስጥ በደንብ ለማየት የማያስችል (የሚከለክል) የአይን በሽታ::

ዳፍንታም ቅ 1. ዳፍንት የያዘው ሰው:: 2. (ዘይ.) ሀ. ንቃት፥ ቅልጥፍና የሌለው:: ለ. ደደብ፥ ትምህርት የማይገባው::

ዴ የ "**ደ**" ፊደል ሃምስ ዘር::

ዴሲማል ስ ከነጥብ በኋላ የሚፃፍ በአንድና በዜሮ መካከል ያለ ማንኛውም ቁጥር፥ አስርዮሽ ወይም በአስርዮሽ፥ በመቶኛ፥... የሚገለፅ ክፍልፋይ ቁጥር፥(ለምሳሌ 0.27 ዴሲማል ቁጥር ሲሆን ሃያ ሰባት መቶኛ የሚለውን አሃዝ ያሳያል ወይም ይወክላል)::

ዴሲ ሜትር ስ የርዝመት መለኪያ፥ 10 ዴሲ ሜትር 1 ሜትር ይሆናል::

ዴፈረንሺያል (ዲፈሬንሻል) ስ ሁለቱን የመኪና የኋላ እግሮች ፍጥነት ለማስተካከያነት የሚረዳ የመኪና አካል::

ድ የ"**ደ**" ፊደል ሳድስ ዘር::

ድሁር ቅ በጣም አጭር (ሰው)::

ዴሂት ስ 1. አጭርና ቀጭን የሆነች የዋልታ ዙሪያ ማገር:: 2. የቂጥኝ አይነት::

ድሃ "**ደሃ**" ን ተመ.

ድህንፃ ስ የበገና፥ የክራር ጅማት መገረፊያ:: (የበገናን ስእል ተመ.)::

ድለላ^{1} "ደለለ " ስር ተመ.

ድለላ^{2} "ደለ^{2}" ስር ተመ.

ድለቃ "ደለቀ^{1}" ስር ተመ.

ድላል "ደለለ^{2} " ስር ተመ.

ድል ስ ተፎካካሪን፥ ተቀናቂን፥ ጠላትን፥.. በማሸነፍ፡ በመርታት የሚገኝ ውጤት።

ድል ሆነ/ተነሳ ተሸነፈ።

ድል መታ/ነሳ/ አደረገ/ ተቀዳጀ/ አሸነፈ፡ የበላይነት አገኘ፥ ረታ፥ ።

ድልሀ "ደለሀ" ስር ተመ.

ድልምጥ "ደለመጠ" ስር ተመ.

ድልቂያ "ደለቀ^{1}" ስር ተመ.

ድልብ "ደለበ" ስር ተመ.

ድልዝ^{1} " ደለዘ^{1} " ስር ተመ.

ድልዝ^{2} "ደለዘ^{2} " ስር ተመ.

ድለዳል "ደለደለ" ስር ተመ.

ድልድል ዝ.ከ.

ድልድል ዝ.ከ.

ድልድይ ስ በወንዝ ወይም የወንዝ ቅርፅ ባለው መሬት ላይ ከእንጨት፡ ከድንጋይ፥ ከብረት፥... የሚሰራ መሸጋገሪያ።

ድሉት "ደላ" ስር ተመ.

ድመት ስ ብዙውን ጊዜ አይጥ እንዲያድን ተብሎ በቤት ውስጥ እንዲኖር የሚደረግ፥ፀጉሩ ልስልስ የሆነ ትንሽ የቤት እንስሳ(ስእሉን የቤት እንስሳ ስር ተመ.)።

ድማሚት "ደማሚት" ን ተመ.

ድም

ድም አለ ግ እንደ ከበሮ ወይም እንደ መድፍ ጩሀት ያለ ድምፅ አሰማ፥ ግም አለ።

ድምር "ደመረ" ስር ተመ.

ድምበር "ደነበረ^{3}" ስር "ድንበር"ን ተመ.

ድምበርተኛ""ደነበረ^{3}" ስር "ድንበርተኛ" ን ተመ.

ድምቡሉ(ድንቡሉ) ስ 1. ባለ አምስት ሳንቲም መሃለቅ። 2. (ዘይ) ድንቡጭ ያለችና ደመግቡ የሆነች ልጅ እግር ሴት።

ድምቡሽ(ድንቡሺ) ቅ የፋፋ፥ ያማረበት (ህፃን ልጅ)።

ድምቡሮ ዝ.ከ.

ድምቢጥ "ድንቢጥ" ን ተመ.

ድምብላል ስ መጠኑ እንደ ዘንጋዳ የሆነ ዱቡልቡል የቅመም አይነት።

ድምብል "ድንብል" ን ተመ.

ድምድማት "ደመደመ" ስር ተመ.

ድምጥማጥ

ድምጥማጡ ጠፋ 1. ደብዛው ጠፋ፥ ያለበት፥ አድራሻው ታጣ። 2. ተደመሰሰ።

ድምፅ(ድምጥ) ስ 1. በመናገር፥ በማዜም፥ በእንቅስቃሴ አማካይነት ወይም አንድ አካል ከሌላው ጋር ሲላተም የሚፈጠርና ጆሮ ሊሰማው የሚችል ማንኛውም ስርአት የተከተለ ጩሀት ። 2. አንድን ጉዳይ፥ሃሳብ፥... በመደገፍ.. ወይም በመቃወም ወይም ሌላ አቋም በመያዝ የራስን ውሳኔ፥ምርጫ በይፋ (እጅ በማውጣት) ወይም በምስጢር (ካርድ በመጣል) የማሳወቅ፥ የማስመዝገብ ሁኔታ።

ድምፁ አይሰማም ዝምተኛ፥ጭምት ነው።

ድምፁ ያምራል ጥሩ ድምፅ አለው።

ድምፁ ጠፋ 1. ዝም አለ። 2. አድራሻው ታጣ።

ድምፁን ሰለበው ድምፁን ዘጋው።

ድምፅ ሰጠ 1. በምርጫ ወይም በውሳኔ ጊዜ ድጋፉን ወይም ተቃውሞውን እጅ በማውጣት ወይም በሌላ ዘዴ አሳወቀ። 2. ድምፁ እንዲጨምር፥ እንዲጎላ አደረገ (የሬዲዮ፥የቴሌቪዥን)። 3. ድምፅ አሰማ።

ድምፅ ሰጪ ስ መራጭ (ድምፅ በመስጠት)።

ድምፀ መረዋ ቅ ጥሩ ድምፅ ያለው ሰው።

ድምፀ ተአቅቦ ስ በስብሰባ ላይ ለሚተላለፍ ውሳኔ የድጋፍ ወይም የተቃውሞ ድምፅ አለመስጠት።

ድምፅ መቅጃ ስ ማንኛውንም ድምፅ (ጩሀት፥ንግግር፥ዜማ፥...) እየተቀበለ በክር ጥብጣብ ወይም በሸክላ ላይ እንዳለ መዝግቦ ወይም ቀርፆ የሚያስቀር መሳሪያ።

ድምፅ ማጉያ ስ የአንድን ነገር ድምፅ እየተቀበለ መልሶ እንደአስፈላጊነቱ የድምፁን ሃይል ጨምሮና አጉልቶ የሚያሰማ መሳሪያ።

ድምፅ የሌለው መሳሪያ ስ እንደ ጩቤ፥ ጎራዴ፥ ሰንጢ፥... ያለ የጦር መሳሪያ።

ድምፃዊ ቅ 1. ሲያዜም ወይም ሲዘፍን ድምፁ የሚያምር፥ ደስ የሚል። 2. ዘፋኝ።

ድረስ "ደረሰ^{1}" ስር ተመ.

ድሪ ስ ከብር ወይም ከወርቅ የሚሰራ የአንገት ጌጥ።

ድሪ ""ደራ^{1} ስር "ድሪያ" ን ተመ.

ድሪቶ "ደረተ" ስር ተመ.

ድሪቷም ዝ.ከ.

ድሪያ ""ደራ^{2} " ስር ተመ.

ድራማ ስ በቲአትር ቤት፥በሬዲዮ፡ በቴሌቪዥን የሚቀርብ ወይም የቀረበ ተውኔት።

ድራማ ስ ያልተወቃ የዘንጋዳ ወይም የማሽላ ራስ ክምር።

ድራር^1 ስ አስከሬን ወይም የሬሳ ሳጥን መቃብር ውስጥ ከገባ በሃላ አፈር እንዳይጫነው ከለላ የሚሆን የእንጨት ወይም የድንጋይ ርብራብ።

ድራር አቃፊ ስ በመቃብር ውስጥ በሬሳ ሳጥን ዙሪያ የሚደረደርና ርብራቡን (ድራሩን) የሚሸከም ድንጋይ።

ድራር^2 ስ የትልቅ በአል ዋዜማ።

ድራሽ " **ደረሰ**^{1} " ስር ተመ.

ድራብ "**ደረበ**" ስር "**መደረቢያ**" ን ተመ.

ድራት " **ደራ**^{1} " ስር ተመ.

ድራፍት[**ቢራ**] ስ በፋብሪካ ተጠምቆ እንደ ወጣ፡ ብዙ ሳይቆይ በትኩሱ ለተጠቃሚ የሚቀርብ ቢራ ።

ድር "'**ደራ**^{2} " ስር ተመ.

ድርሰት "**ደረሰ**^{2} " ስር ተመ.

ድርሳን ዝ.ክ.

ድርስ "**ደረሰ**^{1} " ስር ተመ.

ድርሻ ዝ.ክ.

ድርቀት "**ደረቀ**" ስር ተመ

ድርቄ ስ ሰገባ።

ድርቅ "**ደረቀ**" ስር ተመ.

ድርቅና ዝ.ክ.

ድርቆሽ ዝ.ክ.

ድርበብ "'**ደረበበ**" ስር ተመ.

ድርብ "**ደረበ**" ስር ተመ.

ድርብብ "'**ደረበበ**" ስር ተመ.

ድርት "**ደረተ**" ስር ተመ.

ድርያ "**ደራ**^{1} " ስር "**ድሪያ**" ን ተመ.

ድርድር "**ደረደረ**" ስር ተመ.

ድርድር ዝ.ክ.

ድርጅት "**ደረጀ**" ስር ተመ.

ድርገት ወረዱ ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) በቅዳሴ ስነ ስርአት ማብቂያ ላይ ምእመናኑን ለማቁረብ መስዋእቱን ይዘው ቀዳሲያኑ በአንድነት ከመቅደስ ብቅ አሉ።

ድርጊት "*ደረገ" ስር ተመ.

ድርጎ "**ዳረገ**" ስር ተመ.

ድርጎኛ ዝ.ክ.

ድርጭት ስ አሸዋማ መልክ ያለውና ከርግብ አነስ የሚል የወፍ አይነት።

ድርፋጭ "**ደረፈጨ**" ስር ተመ.

ድሮ "**ዱሮ**" ን ተመ.

ድስት ስ ወጥ ለመስሪያ ወይም ለመቀቀያ እንዲያገለግል ከሸክላ ወይም ብረት ነክ ከሆኑ ነገሮች የሚሰራ፥የተለያየ መጠን ያለው እቃ።

ድቀት ስ 1. ክስረት። 2. ውርደት።

ድቁስ "**ደቆሰ**" ስር ተመ.

ድቁና " **ዲቆነ**" ስር ተመ.

ድቃቂ "**ደቀቀ**" ስር ተመ.

ድቅን "**ደቀነ**" ስር ተመ.

ድቅድቅ "**ደቀደቀ**^{1} " ስር ተመ.

ድቋ ስ በጉሽ ጠላ መልክ የሚዘጋጅ የጠላ አይነት።

ድቡልቡል "**ድብልብል**" ን ተመ.

ድቡሽት ስ ሲረግጡት ትምክ ትምክ የሚል አሸዋማ መሬት።

ድባ ስ ድቡልቡል ቅርፅ ያለው የዱባ አይነት።

ድባቅ

ድባቅ መታ አጠፋ፥ አወደመ፤ አሸነፈ፥ ደመሰሰ።

ድባብ ስ ከሃር ጨርቅ የሚሰራና የብር ወይም የወርቅ መርገፍ ያለበት፥ በበአል ቀን በቤተክርስቲያን ሊታቦት የሚዘረጋ ትልቅ ጥላ።

ድባኖ "**ደበነ**" ስር ተመ.

ድቤ ስ ለመቃብር ተብሎ የተቆፈረ አፈር።

በድቤ ተቀበረ ያለ ሳጥን ወይም ያለ ድራር ተቀበረ(አስከሬኑ አፈር ብቻ ለበሰ)።

ድቤ ስ ትንሽ ነጋሪት፤ የቃልቻ ከበሮ።

ድብ^1 ስ ረጅም ፀጉርና ጥፍር ያለው፥ ጠንካራና ሃይለኛ የሆነ አውሬ።

ድብ^2

ድብ አለ ግ ወደቀ፥ ዱብ አለ።

ድብ አደረገ ግ አፈረጠ፥ ጣለ።

ድብል^1 "**ደበለ**" ስር ተመ.

ድብል^2 "**ደበለለ**^{2} " ስር ተመ.

ድብልቅ "**ደባለቀ**" ስር ተመ.

ድብልቅልቅ ዝ.ክ

ድብልብል "'**ደበለበለ**" ስር ተመ.

ድብርቅ ስ መድሃኒትነት አለው የሚባል፥ ፍሬው ተወቅጦና ከአጥሚት ጋር ተፈልቶ የሚጠጣ፥ በወይና ደጋ የሚበቅል የእፅዋት አይነት።

ድብርት "ደበረ^3 "

ድብስብስ "ደበሰ" ስር ተመ.

ድብቅ "ደበቀ" ስር ተመ.

ድብብቆሽ ዝ.ከ

ድበት ስ ትንሽ የእህል ክምር።

ድብትርና "ደበተረ" ስር ተመ.

ድብኝት ስ 1. ከጭቃ የተሰራ የእህል ማስቀመጫ፤ ጎታ ጉስጉሻ። 2. (ዘይ.) አጭርና ወፍራም የሆነ (ሰው)።

ድብኝት 1ኛ ፍች

ድብክብክ "ደበከበከ" ስር ተመ.

ድብደባ "ደበደበ^1 " ስር ተመ.

ድብዳብ ስ ለመቀመጫነት የሚያገለግል ከነፀጉሩ የተለፋ የበግ ቆዳ።

ድብደባ ስ የአፈር፤ የጉድፍ ክምር፤ ኩይስ።

ድብድብ "ደበደበ" ስር ተመ.

ድብድብ "ደበደበ^2 " ስር ተመ.

ድንስር "ደነሰረ" ስር "ደንሰረ"ን ተመ.

ድንቁርና "ደነቀረ"ስር ተመ.

ድንቅ "ደነቀ" ስር ተመ.

ድንቅፍቅፍ "*ደነቀፈ" ስር "ደንቀፍቃፋ"ን ተመ.

ድንበር "ደነበረ^3" ስር ተመ.

ድንበርተኛ ዝ.ከ

ድንቡሉ "ድምቡሉ"ን ተመ.

ድንቡሽ "ድምቡሺ"ን ተመ.

ድንቢጥ (ድምቢጥ) ስ መጠኗ አነስተኛ የሆነ የወፍ አይነት።

ድንብል (ድምብል) ስ ሴቶች በክር ሰክተው አንገታቸው ላይ የሚያደርጉት ተሰበት።

ድንብርብር "ደነበረ^2" ስር ተመ.

ድንት አለም ዝንት አለም ።

ድንች ስ የፍሬው ቅርፅ ክብ ወይም ሞላላ ሆኖ በመሬት ውስጥ እንደ ሽንኩርት የሚያፈራና የሚፋፋ፤ ተቀቅሎ፤ ተጠብሶ፤... የሚበላ ተክል።

ድንን ስ 1. ችፍግ ብሎ የሚገኝ ደን። 2. (ዘይ.)ችፍግ ያለ ፀጉር።

ድንኩል

ድንኩል ድንኩል አለ ግ ድክ ድክ አለ (የህፃን ልጅ አካሄድ)።

ድንክ ቅ ከመሰሎቹ በተለየ በጣም አጭር የሆነ ትክለ ሰውነት ያለው።

ድንክ አልጋ ስ አጠር፤ ጠበብ ብሎ ለመቀመጫም እንዲያገለግል ሆኖ ከእንጨትና ከጠፍር የሚሰራ አልጋ።

ድንኳን ስ ከሸራ ወይም ከአቡጀዲ፤... የሚሰራ፤ እንደ ቤት ሆኖ በጊዜያዊነት የሚያገለግል መጠለያ።

ድንኳን

ድንኳን ጣለ (ተከለ) ድንኳን ዘረጋ።

ድንገት ተው.ግ 1. ሳይታሰብ። *ሰውዬው ድንገት ሞተ*። 2. ምናልባት።*ድንገት መኪና ካላገኘሁ ነገ እሄዳለሁ*።

ድንገተኛ ቅ 1. ያልታሰበ። ስ 2. ድንገት የሚያጋጥም የህመም አይነት። 3. ድንገተኛ ለተባለው በሽታ ማስታገሻ ይሆናል የሚባል መድሃኒት(ብዙውን ጊዜ ስራስር)።

ድንገተኛ ክፍል ስ ድንገት የታመሙ ወይም አደጋ ያጋጠማቸው ሰዎች የሚታከሙበት ክፍል (ሃኪም ቤት)

ድንጉላ[ፈረስ] ስ ያልተኮላሸ ፈረስ።

ድንጉል ስ 1. ከአንድ የንብ መንጋ መካከል ስራው ውሃ ማጋዝ የሆነና የማይናደፍ ንብ ። 2. ድንጉል ከሚባለው የንብ ድምፅ ጋር የሚመሳሰል ወፍራም ድምፅ የሚወጣው የበገና ቅኝት።

ድንጉርጉር "ደነጎረ^2 " ስር ተመ.

ድንጉጥ "ደነገጠ" ስር ተመ.

ድንጋሌ "ድንጋል" ስር ተመ.

ድንጋይ(ደንጊያ) ስ 1. ብረትነት የሌለው ጠጣር የማእድን አይነት። 2. (ዘይ.)ደደብ፤ ነገር የማይዘልቀው፤ ጠንካራ፤ቻይ። 3. "ባትሪ" ስር " ባትሪ ድንጋይ"ን ተመ.

ድንጋይ ነው ደደብ፤ የማይገባው ነው።

የድንጋይ ልብስ ስ በድንጋይ ላይ ተለጥፎና ሠርቶ ብሎ የሚበቅል አረንጓዴ የእፅዋት አይነት።

የድንጋይ ከሰል ስ እየነደደ ሙቀት

የሚሰጥና ጋዝ የሚገኝበት ጥቁርና ጠጣር ማእድን።

ድንጋይ ልብ (ልበ ድንጋይ) 1. ጨካኝ። 2. የማይገባው። *ድንጋይ ልብ ስለሆነ ቢነግሩት ሊገባውም።*

ድንጋይ ራስ ደደብ።

ድንጋይ በእግሩ ሰነፍ፣ ቅልጥፍና የሌለው ጎታታ።

ድንጋያማ ቅ ድንጋይ የበዛበት ቦታ ወይም መሬት።

ድንጋጌ "ደነገገ" ስር ተመ.

ድንጋጤ "ደነገጠ" ስር ተመ.

ድንግል (ብ.ቁ.**ደናግል**) ስ 1. ድንግልና። 2. የግብረ ስጋ ግንኙነት ፈፅሞ ያላደረገ። ቅ 3. ታርሶ፣ ተቆፍሮ የማያውቅ (መሬት)።

ድንጋሌ ስ ንፅህና፣ ህይወትን በሙሉ የግብረ ስጋ ግንኙነት ፈፅሞ ሳያደርጉ የመኖር ሁኔታ።

ድንግላዊ (ድንግላይ) ቅ ህይወቱን በሙሉ ከግብረ ስጋ ግንኙነት ርቆ የሚኖር።

ድንግልና ስ 1. ክብረ ንፅህና፣ ህግ። 2. ከግብረ ስጋ ግንኙነት ርቆና ተጠብቆ የመኖር ሁኔታ።

ድንፋታ "ደነፋ" ስር ተመ.

ድኝ ስ ቀለሙ ቢጫ የሆነ የማእድን አይነት።

ድከን "ደከነ" ስር ተመ.

ድኩላ ስ አንገቱ ነጭ፣ በጀርባው ላይ አልፎ አልፎ ነጣ ያሉ ምልክቶችና ጥቁር ሸንትር ያለው፣ ሌላ አካሉ ወርቅማ የሆነ፣ ከኢጋዘንና ከኒያላ ወገን የሚመደብ፣ ቀንዶቹ እስከ 50 ሳንቲ ሜትር የሚረዝሙ፣ ቅጠላቅጠል፣ ሳር፣... የሚመገብ የዱር እንስሳ (ስእሉን "የዱር እንስሳ" ስር ተመ.)።

ድኩም "ደከመ" ስር ተመ.

ድካ "ደካ^{1}" ስር ተመ.

ድካም "ደከመ" ስር ተመ.

ድክመት ዝ.ክ.

ድክን "ደከነ " ስር "**ድከን** " ን ተመ.

ድኮት ስ ከብር ወይም ከነሃስ የሚሰራ እንደ አንባር ያለ የእግር ጌጥ።

ድኳ "ደኳኳ "ን ተመ.

ድው^{1}

ድው አለ ግ ፀጥ፣ እረጭ አለ።

ድው አለው ፍዝዝ፣ ቅዝዝ አደረገው።

ድው^{2}

ድው አለ ግ ግው የሚል ድምፅ አሰማ።

ድውር "ደወረ" ስር ተመ.

ድውይ "ደዌ" ስር ተመ.

ድድ ስ በጥርሶች መብቀያ፣ ጥርሶችን አጥብቆ የሚይዝ ስጋ።

ድዱን አስጣ ገለፈጠ፣ በሆነ ባልሆነ ነገር ሳቀ።

ድዳም ቅ (ስድብ) 1. ከተለመደው መጠን በላይ ድዱ ከጥርሶቹ ጎልቶ የሚታይ ሰው። 2. በሆነ ባልሆነ ነገር የሚስቅ፣ የሚገለፍጥ።

ድድር "ደደረ" ስር ተመ.

ድድቅ "ደደቀ" ስር ተመ.

ድጅኖ ስ ሁለቱም ጫፎቹ ድንጋይ ለመፈንቀል፣ መሬት ለመማስ እንዲያገለግል ሆኖ ሙሉ በሙሉ ከብረት የተሰራ መሳሪያ።



ድጅኖ

ድጉልጉል "*ደጎለጎለ" ስር ተመ.

ድጉስ "ደጎሰ" ስር ተመ.

ድጋሚ "ደገመ^{1}" ስር ተመ.

ድጋም "ደገመ^{2}" ስር ተመ.

ድጋፍ "ደገፈ" ስር ተመ.

ድግ "*ደገደገ" ስር ተመ.

ድግምተኛ "ደገመ^{2}" ስር ተመ.

ድግምታም ዝ.ክ.

ድግምት ዝ.ክ.

ድግር ስ ከሞፈር ቂጥ ጋር በቅትርት ከእርፍና ከማረሻ ጋር በወገል የሚያያዝና ማረሻ የሚሰነጠቀውን መሬት እያሰፋ የሚሄድ የእርሻ መሳሪያ(ስእሉን ሞፈር ስር ተመ.)።

ድግስ "ደገሰ" ስር ተመ.

ድግዝግዝታ "*ደገዘ" ስር ተመ.

ድግድግ ዝ.ክ.

ድግግም "ደገመ^{1}" ስር ተመ.

ድግግሞሽ ዝ.ክ.

ድግጣ ስ የግንዱ ውፍረት እንደ ጨፌቃ ሆኖ መሰል መሰል ያለ፣ በወይና ደጋ የሚበቅል የእፅዋት አይነት።

ድጎማ "ደጎመ" ስር ተመ.

ድጓ^{1} ስ ያሬድ ከደረሳቸው መካከል ትልቁ የዜማ መፅሃፍ።

ድጓ^{2} ስ ደቃቅ ገለባ እብቅ።

ድጣም "ዳጠ" ስር ተመ.

ድጥ ዝ.ከ.

ድጦሽ ስ ተቀቅሉ የተደፈጠጠ ምስር፥ የአተር ክክ።

ድፊት ስ ወፍ፡ ቆቅ፡... ለመያዝ የሚያገለግል እንደ ወንፊት ያለ፥ ቅርጫት መሰል ወጥመድ።

ድፍርሳ ስ መልኩ ግራጫማ ቡና ቀለም የሆነ፥ በአንገቱ ዙሪያ፥ ከቂጡ አካባቢና ከየኩቴዎቹ በላይ እንደ ቀለበት የዞሩ ነጫጭ ሽንትሮች ያሉት፥ ቆዳው መጥፎ ጠረን የሚያመነጭ፥ እንደ ደጋን ጎበጥ ያሉ ቀንዶች ያሉት ባረቢል የዱር እንስሳ፡፡

ድፋት "ደፋ" ስር ተመ.

ድፌት ዝ.ከ.

ድፍረት "ደፈረ" ስር ተመ.

ድፍርስ "ደፈረሰ" ስር ተመ.

ድፍን "ደፈነ" ስር ተመ.

ድፍንፍን ዝ.ከ.

ድፍድፍ "ደፈደፈ" ስር ተመ.

ድፍጥ "ደፈጠጠ" ስር "ደፍጣጣ" ን ተመ.

ድፍጥጥ ዝ.ከ.

ድፎ "ደፋ" ስር ተመ.

ዶ የ "ደ" ፊደል ሳብእ ዘር።

ዶለ ግ ከተተ፥ ወመረ፥ አገባ።

ዶለተ ግ 1. አሴረ፥ አደመ። 2. ተሰበሰበ (ለምክክር)።

ዱለታ(ዱለት) ስ ሴራ፥ አድማ።

ዱለተኛ ቅ አድመኛ፥ ሴረኛ።

ዶለዝ ቅ 1. ስለት የሌለው፥ ዱልዱም። 2. ወፍራምና ፍርጥም ያለ ሰውነት ያለው (ሰው)። 3. (ዘይ.) ደደብ፥ ደነዝ፥ እውቀት የማይገባው።

***ዶለዶለ**

ዶልዷሌ ቅ ቸር፥ ለጋስ።

ተንዶለዶለ ግ በብዛት ወረደ፥ ፈሰሰ (ፈሳሽ)።

አንዶለዶለ ግ በብዛት አወረደ፥ አፈሰሰ።

ዶለዶመ ግ ደነዘ፥ ስለት የለሽ ሆነ።

ዱልዱም ቅ 1. ስለት የሌለው፥ ደነዝ። ስ 2. አጠር ብሎ ቸምቸም ያለ የዶሮ ክንፍ።

ዶልዱማ ቅ ስለት የሌለው፥ ደነዝ።

አዶለዶመ ግ ስለትን አደነዘ፥ ዱልዱም እንዲሆን አደረገ።

ዶላር ስ በአሜሪካ፥ በካናዳ፥ በአውስትራሊያ፥... የሚያገለግል የገንዘብ ስም።

ዶልዷሌ "*ዶለዶለ" ስር ተመ.

ዶልዷማ "ዶለዶመ" ስር ተመ.

ዶማ ስ እጀታ ያለው መቆፈሪያ።



ዶማ

ዶመኛ ስ 1. በሬ ስለሌለው የእርሻ መሬቱን እየቆፈረ በማምረት የሚተዳደር ሰው። 2. በዶማ የሚቆፍር።

***ዶረረ**

ዱርር ቅ ጅንን፥ ኩሩ።

ተዶረረ ግ 1. ኮራ፥ ተጀነነ። 2. ተቆጣ፥ አኮረፈ።

ተዶራሪ ቅ ኩሩ፥ ጅንን።

አዶረረ ግ አኮረፈ፥ ተቆጣ።

ዶሮ ስ 1.የሚረባ፥ ስጋው ለምግብነት የሚያገለግል፥ የአሞራ ወገን የሆነ የቤት እንስሳ(ስእሉን የ"ቤት እንስሳ" ስር ተመ.)። 2. (ዘይ.) ደቃቃ የሆነ፥ አቅም የሌለው (ሰው)።

የዶሮ ብልት ስ ዶሮ ከተገነጣጠለ በኋላ የሚወጣው እንደ መላላጫ፥ ፈረሰኛ፥...ያለው የዶሮ አካል።

ዶሮ ጮሀ አኩለ ሊሊት ሆነ።

ዶሮ ማታ 1. አንድ ሰው አንድን ከበድ ያለ ነገር ፈጥኖ እንዲፈፅም(ለምሳሌ መራራውን ኩሶ ጅው አድርጎ እንዲጠጣ) የሚነገር የማደፋፈሪያ ቃል። 2. ባዶ ተሰፋ።

ዶሮ በጋን 1. በጣም ትንሽ ለሆነ ነገር በጣም የተለቀ መከተቻ፥ መያዣ ማድረግ። 2. እጅግ አለመጠን ያነሰ።

የዶሮ ማር ስ ከገረንገሬና ከአምጃ እንጨት ላይ የሚገኝ ማር የሚመስል ሙጫ።

የዶሮ ብልት ስ እንደ ፈረሰኛ፥ መላላጫ፥... ያለ የዶሮ ስጋ።



የዶሮ ብልት

[የ] ዶሮ ወጥ ስ ከዶሮ ብልት ብቻ የተዘጋጀ ወጥ።

ዶሮ ዳቦ ስ ሊጡ በዶሮ ወጥ ተለውሶ ከእንቁላሉና አጥንቱ ጋር አብሮ የተጋገረ የአበሻ ዳቦ።

ዶሰኛ ቅ ሃይለኛ፥ ጉልበተኛ።

ዶሴ ስ ማህደር፥ ፋይል።

ዶሴ ከፈተ ፋይል ከፈተ፥ ሙግት ጀመረ።

*ዶሸዶሸ

ዶሸዶሸ አለ ግ ተንዶሸዶሸ፥ ተንጦሸጦሸ።

ዶሸዶሸ አደረገ አንዶደሸዶሸ፥ አንጦሸጦሸ።

ተንዶሸዶሸ ግ 1. በውሃ የራስ ጥሬ (ሽንብራ፥ ባቄላ፡..) ሲቆላ የሚሰጠውን አይነት ድምፅ ሰጠ። 2. ተቆላ (የራስ ባቄላ፡ አተር፡...)።

አንዶሸዶሸ ግ 1. በውሃ የራስ ጥሬ ሲቆላ የሚሰጠውን አይነት ድምፅ እንዲሰጥ አደረገ። 2. ቆላ (የራስ ባቄላን፥ አተርን፥...)።

እንዱሽዱሽ ስ በውሃ በጣም ከራሰ በኋላ የተቆላ ጥሬ (ባቄላ፡ አተር፥...)።

ዶቃ ስ ብዙውን ጊዜ ጥቁር ሰማያዊ ቀለም ያለውና ቅርፁ እንደ ወፍራም ቀለበት የሆነ፥ መጠኑ ከቀለበት ያነሰ፥ በክር ተሰክቶ አንገት ላይ በጌጥነት የሚንጠለጠል ከጠርሙስ የሚሰራ የልጆች ጌጥ።

ዶቅማ ስ ጥቁር ፍሬ የሚያፈራና ፍሬውም የሚበላ ጠንካራ የሆነ የዛፍ አይነት፤ ፍሬውም ዶቅማ ይባላል።

*ዶበረ

አዶበረ ግ ተከፋ፡ ተቀየመ፡ አኮረፈ።

አስዶበረ ግ አስከፋ፡ አስቀየመ፡ አስኮረፈ።

ዶቢ ስ የሳማ አይነት።

ዶኩሜንት ስ በምስክርነት ወይም በማስረጃነት ሊያገለግል የሚችል ማንኛውም የፅሁፍ መረጃ፥ ሰነድ።

ዶኩሜንታሪ ፊልም ስ የሰዎችን የአኗኗር ዘዴ፥ የእለት ተእለት የስራ እንቅስቃሴና ውጤት፤ የእንስሳትን አኗኗር፥ ጠባይ፥...፤ የተፈጥሮ አካባቢን ሁኔታ የሚያሳይ ጥናታዊ ወይም ዘጋቢ ፊልም።

ዶኬ "*ዶከደከ" ስር ተመ.

ዶክተር ስ 1. የህክምና ሳይንስ ምሩቅና በህክምና ስራ ላይ የተሰማራ ባለሙያ። 2. በማንኛውም የእውቀት ዘርፍ ዩኒቨርሲቲ የሚሰጠውን ከፍተኛውንና የመጨረሻ ደረጃ የሆነውን ሶስተኛ ዲግሪ የተቀበለ ሰው።

ዶዮ ስ (የን.አነ.) ቅመም፡ ቅባት፡... የሌለበት መናኛ ወጥ።

ዶግ ስ ጥንካሬ የሌለው፥ ቅጠሉ እንስሳል የሚመስል የእፅዋት አይነት።

[የ] ዶግ አመድ አደረገ አወደመ፡ አጠፋ።

ዶግማ ቅ በጥቁርና በቀይ መካከል ያለ የከብት መልክ።

ዶጮ ስ 1. መጠኑ አነስተኛ የሆነ የገንቦ አይነት። 2. (ዘይ.) አጭርና ወፍራም የሆነ (ብዙውን ጊዜ ለልጅ)።

ዶፈ ግ ከነፋስ ጋር የተቀላቀለ ሃይለኛ ዝናብ ያለማቋረጥ ጣለ፥ ዘነበ።

ዶፍ ስ ነፋስ ቅልቅል የሆነና ለረጅም ሰአት ያለማቋረጥ የሚዘንብ ሃይለኛ ዝናብ።

ዶፈዶፈ ግ ገዘፈ፥ ወፈረ።

ዶፈዶፍ (ዶፍዶፋ) ቅ ወፍራም፡ ቅርፀቢስ፡ ከመወፈሩ የተነሳ ቅርፁ የማያምር፥ የተድበለበለ።

ዶፍ "**ዶፈ**" ስር ተመ.

ዶፍዷፋ "**ዶፈዶፈ**" ስር ተመ.

ዷ^1 የ "ዷ" ፊደል ፍንዕቅ ዘር።

ዷ^2

ዷ አለ ግ እንደ ጥይት ጮሀ ወይም እንደ ቦንብ ፈነዳ።

ዷ አደረገ ግ እንደ ጥይት ተኩስ ወይም እንደ ቦንብ ፍንዳታ ያለ ድምፅ አሰማ፥ አጮሀ።

ተንዷዷ ግ በተደጋጋሚ የተኩስ ወይም የፍንዳታ ድምፅ ሰጠ ወይም ተሰማ።

አንዷዷ ግ ተከታታይ የሆነ የፍንዳታ ወይም የተኩስ ድምፅ አሰማ።

ጀ

ጀ ከ"ደ" ፊደል ስር ቀጥሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል (ግእዙ ሆሄ)።

ጀለ ግ ቋለ፤ ሞኝ ሆነ።

ጅል ቅ ቂል፤ ሞኝ።

ጅላጅል ቅ ቂላቂል፤ ሞኛሞኝ፤ ወደ ቂልነት የሚወስደው።

ተጃጃለ ግ 1 ቂል፤ ሞኝ ሆነ። 2 ተሞኘ።

አጀለ ግ አቄለ፤ አሞኘ።

አጃጃለ ዝ.ከ.

ጀለተ (ዠለተ) ግ በዛ፤ ሰፋ፤ ተንሰራፋ (አትክልት፤ ፀጉር)።

***ጀለጀለ**

ጀልጃላ ቅ አለቅጥ የረዘመ፤ ዘልባላ (ብዙውን ጊዜ ለልብስ)።

ጅልጅል አለ ግ ተንጀለጀለ፤ ተንዘረፈፈ።

ተንጀለጀለ ግ ያለቅጥ ረዘመ፤ ተንዘረፈፈ።

ተንጀላጀለ ዝ.ከ.

አንጀለጀለ ግ ያለቅጥ አረዘመ ወይም አስረዘመ (ብዙውን ጊዜ ለልብስ)።

አንጀላጀለ ዝ.ከ.

ጀለጠ "ዠለጠ"ን ተመ.

ጀላ ስ (ነውር) የወንድ ብልት።

ጀሌ ስ 1. የጦር መሳሪያ ያልያዘ ዘማች። ቅ 2. ተራ ህዝብ ። 3. መሪ ያልሆነ፤ ተከታይ፤ ወይም ተራ አባል (የእንቅስቃሴ፤ የድርጅት)።

ጀልባ ስ መጠኑ አነስተኛ የሆነ የውሃ ላይ መጓጓዣ። (ስእሉን "መጓጓዣ" ስር ተመ.)

ጀልጃላ "*ጀለጀለ" ስር ተመ.

ጀመለ ግ በብትን፤ በዝርዝር የነበረውን በአንድነት አደረገ።

ጅምላ ስ ጥቅል፤ ያልተበተነ፤ በአንድነት የሆነ።

በጅምላ ተው.ግ 1. በጥቅል፤ በነጠላ ያልሆነ (የሸቀጣ ሸቀጥ ግብይትና አሻሻጥ መንገድ)። 2. በአጠቃላይ። *ሁሉም ሰራተኛ በጅምላ ሰነፍ አይባልም።*

ጅምላ ነጋዴ(ሻጭ) ስ ሸቀጦችን በችርቻሮ ሳይሆን በጥቅል የሚሸጥ ነጋዴ፤ አከፋፋይ።

ጀመረ ግ 1. አንድን ስራ፤ ተግባር ለመስራት እንደ ብሉ ከመነሻው ተነሳ። 2. አንድን ስራ፤ ድርጊት ማካሄድ፤ መስራት ያዘ። *ስራ የምንጀምረው በሁለት ሰአት ላይ ነው።* 3. አንድን ስራ ለማከናወን፤ ለመፈፀም ወጠነ። 4. አንድ ድርጊት መካሄድ ያዘ፤ ወይም አንድ ሁኔታ ድንገት ተከሰተ። *እንባ መውረድ ጀመረ/ዝናብ መዝነብ ጀመረ።* 5. አንድን ነገር ለመስራት፤ ለማውጣት ቀዳሚ ሆነ። *የህትመትን ስራ የጀመረችው ሃገር ትድኒቀላች።* 6. (ነገርን፤ ጠብን፤...) ጫረ፤ ተነኮሰ ወይም ድርጊቱን ለመፈፀም የመጀመሪያው ወገን ሆነ። 7. አንድ ነገር፤ መሳሪያ፤... ተግባሩን ማከናወን ያዘ፤ ወይም አንድ ሁኔታ መሆኑ፤ መካሄዱ ተከሰተ። *ሆቴሉ ስራ ጀመረ።*

መጀመሪያ ስ 1. መነሻ። ተው.ግ. በቅድሚያ፤ በፊት።

ለመጀመሪያ ጊዜ 1. ማንም ሳያደርገው በፊት፤ *ለመጀመሪያ ጊዜ አለምን የዞረ እሱ ነው።* 2. ለአንደኛ ጊዜ። 3. ከዚህ ቀደም ሳይሞከር፤ ሳይደረግ። *ቀለም የቀባሁት ለመጀመሪያ ጊዜ ነው።*

የመጀመሪያ እርዳታ ስ አደጋ የደረሰበት ሰው ሁነኛውን ህክምና እስኪያገኝ ድረስ ለጊዜው የሚደረግለት የመጀመሪያ ህክምና።

ጀማሪ ቅ 1. ቀዳሚ፤ መስራች፤ ቆርቋሪ። 2. ተለማማጅና ለአንድ ስራ ገና አዲስ የሆነ።

ጅማሬ ስ 1. የአነሳስ፤ የአጀማመር ሁኔታ። 2. የመጀመሪያ ደረጃ።

ጅማሮ "ጅምር"ን ተመ.

ጅምር (ጅማሮ) ቅ 1. ያላለቀ፤ ስራው የሚቀጥል፤ የተጀመረ። 2. የአጀማመር ሁኔታ። 3. አንድ ሰው የጀመረውና ያልጨረሰው ስራ። *ጅምሬን ልጨርስ።*

አስጀመረ ግ 1. አንድ ሰው አንድን ስራ እንዲሰራ አያያዘ፤ አቆናጠጠ። 2. አንድ ስራ፤ ጉዳይ፤... እንዲጀመር ወይም ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲሰራ አደረገ።

ተጀመረ ግ 1. መካሄድ፤ መከናወን፤ መሰራት ያዘ። 2. ለመጀመሪያ ጊዜ ታየ፤ ተከሰተ። *የትያትር ጥበብ በሃገራችን ከተጀመረ ሃምሳ አመታት አልፏል።* 3. ተሞከረ። *አልተሳካም እንጂ ተጀምሮ ነበር።*

ጀማ ስ ለአንድ ለተወሰነ ጉዳይ የተሰበሰቡ ሰዎች፤ ጉባኤ።

ጀምበር (ጀንበር፤ ዠምበር፤ ዠንበር) ስ ፀሃይ። *ጀምበር ስትጠልቅ ወደ ቤቱ ይገባል።*

ጀምበር ስትጠልቅ ወደ አመሻሽ ላይ፤ መሸት ሲል።

ጀምብ ስ ከሁለት የቀርቃባ ጭነት አንዱ።

ጀሞ ስ ከብረት የሚሰራና ቅርፁ ሳይዳ ወይም አካፋ የሚመስል እሳት መጫሪያ።

ጀረጀፈ ግ አረጀ፥ ገረጀፈ።

ጀረገገ "ዠረገገ" ን ተመ.

ጀርባ (ዠርባ) ስ 1. ከማጅራት እስከ መቀመጫ ያለ በሆድና በደረት ተቃራኒ አቅጣጫ የሚገኝ የሰውነት ክፍል(ሰውነት ስር ተመ.)። 2. የአንድ ነገር (ወረቀት፣ ሰሌዳ፣ ቤት...) የኋለኛ ገፅታ።

ጀርባውን ሰጠ /አዞረ/ 1. ፊቱን አዞረ። 2. ችላ አለ።

የጀርባ አጥንት ዋነኛ የሆነ፥ በጣም አስፈላጊ ነገር። *ቡና ለአገሪቱ ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት ነው።*

ጀበና ስ ከቆርቆሮ ወይም ከነሃስ ወይም ከሸክላ የሚሰራና ለቡና ለሻይ፥... ማፍያነት የሚያገለግል እቃ።

ጀበደ "ዠበደ" ን ተመ.

ጀባ ግ እነሆ፣ ይህው ወይም እባክዎን ይጋበዙ ለማለት የሚያገለግል ቃል። *አቦል ጀባ።*

ጀባ አለ ግ (ተራ አነ.) ሰጠ።

ጀባ ስ ፀጉሩ ሳይመለጥ የተለፋ የበሬ ቆዳ።

ጀብራራ "* ዠበረረ" ስር "ዠብራራ" ን ተመ.

ጀብዱ(ጀብድ፥ ዠብድ፥ ዠብዱ) ስ የጉብዝና፥ የጀግንነት ስራ።

ጀብደኛ ቅ 1 ጀብዱ የሰራ። 2 ለዝና ሲል ሁኔታዎችን ሳያመዛዝን አጉል የሆነ የድፍረት ስራ የሚሰራ።

ጀቦነ ግ ሸፋፈነ፣ አለበሰ።

ተጀቦነ ግ ጠቅላላ ወይም መላ አካሉን ተሸፈነ።

ጀተሬ "ዠተሬ" ን ተመ.

ጀነቶ ስ የነጭና የቀይ ጠቃጠቆ ያለበት ድቡልቡል ዶቃ።

ጀነነ ግ አኮራ፥ አተበተ።

ጅንን ቅ ኩሩ።

ተጀነነ ግ ኮራ፥ ተቤተ።

ጀነጀነ ግ በብዛት ሰበሰበ፥ አስገባ፥ ጠቀጠቀ።

ተጀነጀነ ግ በብዛት ተሰበሰበ፣ ተጠቀጠቀ።

ጀንበር "ጀምበር" ን ተመ.

ጀንዲ (ዠንዲ) ስ ለመኝታ ንጣፍ የሚያገለግል የተለፋ የበሬ ወይም የላም ቆዳ።

ጀንፈል(ጀፈል) ስ ከነእምቡጡ የሆነ ወይም ያልተፈለፈለ ቡና።

ጀውጃዋ(ዠውዠዋ) ቅ ከውካዋ፣ አቅለቢስ።

ጀዲ[መሬት] ስ በታህሳስ ወር የሚወጣ የኮከብ አይነት። በተጨማሪ "ኮከብ ቆጠራ" ን ተመ.

ጀጀረ ግ የምግብ ፍላጎት አሳጣ።

ጀጀበ ዝ.ከ.

ጀገነ ግ ጎበዘ፥ ደፈረ፥ ጀግና ሆነ።

ጀግና ስ 1. ለሃገር፥ ለወገን መስዋእትነት ከፍሎ ጥሩ ተግባር ያከናወነ፣ ወኔ፥ ድፍረት በሚጠይቅ ሁኔታ ላይ ጀብዱ የሰራ። 2. ብርታት፥ ጥንካሬ በሚጠይቅ ስራ ላይ ችግርን ተቋቁሞ ለውጤት የበቃ ጎበዝ። 3. ወጣት፣ ጎረምሳ።

ጀጎለ ግ አጠረ፥ ቀጠረ፥ አጥር አበጀ።

ጀጎል ስ አጥር፥ ቅጥር።

ጀፈጀፈ ግ ብዙ ቅርንጫፍ አወጣ።

ጀፍጃፋ ቅ ብዙ ቅርንጫፍ፥ ቅጠል ያለው።

ጀፍጀፎ ቅ እጅብ ብሎ በብዛት የበቀለ (ቡቃያ፥ ችግኝ፥...)።

ጁ የ "ጀ" ፊደል ካእብ ዘር።

ጁሆ ስ መያዣ፥ መድን።

ጂ የ "ጀ" ፊደል ሳልስ ዘር።

ጂምናስቲክ ስ ሰውነትን ለማፍታታት፥ ለማዳበር... የሚሰራ የአካል ማስልጠኛ ስፖርት።

ጂምናዚየም ስ ጂምናስቲክ ለመስራት የሚያገለግሉ የተለያዩ መሳሪያዎች ያሉበትና ጂምናስቲክ የሚሰራበት ትልቅ አዳራሽ።

ጂኒ (ጅን) ስ ሰይጣን።

ጂኒው ተነሳበት ቁጣ ቁጣ አለው፥ ተናደደ።

ጂኒያም ቅ (ስድብ) 1. ሰይጣናም። 2. ተናዳጅ።

ጂና ስ 1. የቀንድ ከብት ጅራት። 2. ከበሬ ጅራት ወይም ከዞማና ከፍየል ቅልጥም ላይ ተገፎ እንደጅንፎ ከበትር ወይም ከዱላ ላይ የሚጠለቅ ቆዳ።

ጂኦሎጂ ስ የመሬትን አካል (እንደ ድንጋይ አፈር ማእድን፥... ያሉትን) አፈጣጠርና ምንነት የሚያጠና ሳይንስ፣ የከርሰ ምድር ጥናት።

ጂኦሜትሪ ስ የመስመሮችን፥ የማእዘኖችን፥ የወለሎችን ጠባይና ዝምድና የሚያጠና ሳይንስ።

ጂኦተርማል ስ ከከርሰ ምድር የሚገኝ የተፈጥሮ እንፋሎት ሃይል።

ጂኦግራፊ ስ ስለመሬት ገፅታ፥ ስለአገሮች አቀማመጥ፥ ስለወንዞች፥ ተራሮች፥ አየር ጠባይ

ህዝብ ሁኔታ፥... የሚያጠና ሳይንስ፤ የመልክአምድር ጥናት።

ጃ የ "**ጀ**" ፊደል ራብእ ዘር።

ጃል በንግግር ላይ መገረምን፣ መደነቅን፥ ግራ መጋባትን ለመግለፅ የሚያገለግል ቃል። *ምነው ጃል! እንዲህ አደረግህኝ:*

ጃሉ¹ ስ መሬት ለመቀየስ የሚያገለግል የመሃንዲስ ዘንግ።

ጃሉ²**[መገን]** በሸለላ ወይም በቀረርቶ ጊዜ እንደመግቢያ ሆኖ የሚያገለግል ቃል።

ጃርት ስ አካሉ በአደጋ ጊዜ በየአቅጣጫው እንደጦር በሚወረወር ጫፈ ሹል ነገር የተሸፈነ ድንች ዱባ፣ በቆሎ፥... የሚበላ አውሬ።

ጃርት

የጃርት ወስፌ ስ በጃርት ሰውነት ላይ እንደ ፀጉር የሚበቅል፥ መጠኑ እርሳስ የሚያህል፥ ውስጠ ክፍትና ቀለሙ ዝንጉርጉር የሆነ፣ በአደጋ ጊዜ በየአቅጣጫው እንደጦር የሚወረወር ጫፈ ሹል አካል።

ጃስ አንድን ነገር እንዲያባርር ውሻን ሩጥ፥ ያዝ ለማለት የሚያገለግል ቃል።

ጃንሆይ "ትልቁ!"፥ ገናናው!" በማለት ነገስታትን ለመጥራት የሚያገለግል የአክብሮት መጥሪያ ቃል።

ጃንደረባ (ዣን ደረባ) ስ በጥንት ጊዜ ንግስቲቱን እንዲጠብቅ፥ እንዲያጫውት ተብሎ ቤተመንግስት ውስጥ እንዲቀመጥ ይደረግ የነበረ ስልብ።

ጃንጥላ(ዣንጥላ) ስ 1. ከዝናብ፥ ከፀሃይ ለመከላከል የሚያገለግል ጥላ። 2. ከፍ ካለ ቦታ ወይም ከአየር ወደ ምድር በቀስታ ለመውረድ የሚያገለግል እንደ ጥላ ያለ ነገር፤ ፓራሹት።

በጃንጥላ ወረደ በጃንጥላ (ፓራሹት) አማካይነት ከአውሮፕላን ላይ (ከአየር) ወደ ምድር ወረደ፤ እምድር ላይ አረፈ።

ጃኖ ስ ሰፊ የሆነ ቀይ ጥለት ያለበት ኩታ።

ጃኖ የመሰለ በጣም ቀይ የሆነ።

ጃኬት ስ አጭር ኮት።

ጃዊሳ ቅ 1. አካሉ ግዙፍ የሆነ ጉልበታም(ሰው)። 2. ሆዳም። 3. ቀማኛ፥ ወንበዴ።

ጃዝ[ሙዚቃ] ስ የተለያዩ የሙዚቃ ምት አይነቶችን የሚይዝና በእንቅስቃሴ የተሞላ ነፃ የአጨዋወት ስልት የተላበሰ ዘመናዊ ሙዚቃ።

ጃጀ ግ በጣም ከማርጀቱ፥ የተነሳ አእምሮው በትክክል ማሰብ፥ ማስታወስ፥... ተሳነው።

ጃፖኒ ስ እጅጌ የሌለው ወይም እጅጌው ከትከሻ ላይ የሚቀር ቀሚስ፥ ሸሚዝ፥...።

ጄ የ "**ጀ**" ፊደል ሃምስ ዘር።

ጄላቲ ስ ከተለያዩ የፍራፍሬ አይነቶች የተዘጋጀ ቅመማት፥ ስኳር፥ ውሃ፥ የምግብ ቀለም፥... በአንድነት ተደባልቆ በበረዶ መልክ የሚዘጋጅ ጣፋጭ።

ጄት ስ ፈጣን የአውሮፕላን አይነት።

ጄኔራል ስ በወታደራዊ ክፍል ውስጥ ከሌተና ጄነራል በላይ ያለ ከፍተኛ የጦር መኮንኖች ማዕረግ።

ጅ የ "**ጀ**" ፊደል ሳድስ ዘር።

ጅላጅል "ጀለ" ስር ተመ.

ጅል ዝ.ከ.

ጅማሬ "ጀመረ" ስር ተመ.

ጅማት(ዥማት) ስ 1. የደም ስር። 2. በተለይ ጡንቻማ በሆኑ የስጋ ብልቶች አካባቢ የሚገኝ ስር። 3. ለክራር ለበገና፥ ለደጋን ክር እንዲሆን ተፍቆ የከረረና የደረቀ የፍየል ወይም የበግ አንጀት።

ጅማታም ቅ (ስድብ) በጣም ቀጭን (ሰው)።

ጅምላ "ጀመለ" ስር ተመ.

ጅምር "ጀመረ" ስር ተመ.

ጅረት(ዥረት) ስ ወንዝ።

ጅሬ (ጅር) ስ በአንድ አለቃ (ገመሬ) የሚመራ የዝንጀሮ መንጋ።

ጅራት (ዥራት) ስ 1. በእንስሳት የኋለኛ አካል ላይ የሚገኝ፥ በአብዛኛው በፀጉር የተሸፈነ ተወዛዋዥ የሰውነት ክፍል፥ ጭራ እየተባለም ይጠራል። 2. በቅርፁ ወይም በያዘው ቦታ ጭራ (ጅራት) የመሰለ ነገር። *ጅራት ያለው ኮከብ /የአውሮፕላን ጅራት:*

ጅራት ሆነ መጨረሻ ሆነ፥ ኋላ ቀረ።

ጅራቱን (ጭራውን) ቆላ ተለማመጠ።

ጅራታም ኮከብ ስ ጅራት መሰል ቅጥያ ያለው የኮከብ አይነት።

ጅራፍ ስ ከወደ ጫፉ ቀጭን ሆኖ ከወደ መያዣው ወይም ማንጠልጠያው በኩል እየወፈረ የሚሄድ ከልጥ ወይም ከቃጫ፥... የሚሰራ፥ ሲያወናጭፉት የሚጮህና ለመግረፊያ የሚያገለግል ገመድ፥ ጉንጉን ወይም የተሰፋ ጠፍር።

ጅራፍ

ጅር "ጅሪ" ን ተመ.

ጅርጅር

ጅርጅር አለ ግ ግርግር አለ፡ ወዲያና ወዲህ ተመላለሰ።

ጅስ የቀንድ ከብትን "ሂድ"፣ "ዞር በል" ለማለት የሚያገለግል ቃል።

ጅስም ስ ሰውነት፡ አካል፣ ገላ (ወሎ)።

ጅብ ስ 1.ከትከሻው ከፍ ብሎ ከዳሌው አጠር ያለ፣ መልኩ እንደየዝርያው ቀላ ያለ፡አፈርማ፡ግራጫ፣ አመድማ ሆኖ በአብዛኛው ዥንጉርጉር አለበለዚያም ሽልምልም የሆነ የማሽተትና የማየት ችሎታ ያለው ስጋ በል የዱር አውሬ(ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።2. (ዘይ.)ጉልበተኛ። (ስድብ፡ዘይ.)ሆዳም፣ ስግብግብ።

ጅብ ወሰደው ጅብ በላው።

የጅብ ምርኩዝ ስ በወይና ደጋና በቆላ የሚበቅል የእፅዋት አይነት።

የጅብ ሽንኩርት ሽንኩርት የሚመስልና በዱር የሚገኝ የእፅ አይነት።

[የ] ጅብ ጥላ ስ ቀለሙ ነጣ ያለ፣ ገርንጥላ መሰል ቅርፅ ያለው፡ እንደእንጉዳይ ያለና በመስክ የሚበቅል የእፅዋት አይነት።

ጅብራል ስ አፉ ቀይ፣ ክንፉ በስተላይ በኩል ጥቁር በስተውስጥ ነጭ የሆነ፡ ሃይለኛ ድምፅ ያለው የአሞራ አይነት።

ጅብራ (ዥብራ) ስ ግንዱ ቀጥ ያለና ረጅም፡ ቅጠሉ ሰፋፊ የሆነና በደጋ የሚበቅል በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኝ የእፅዋት አይነት።

ጅን "ጂኒ" ን ተመ.

ጅንን "ጀነነ" ስር ተመ.

ጅንጀሮ "ዝንጀሮ" ን ተመ.

ጅንግላ ስ 1. እንደ እግር ብረት ለማሰሪያ የሚያገለግል ግንድ። 2. የአባያ በሬ መቅጫ ረጅም ግንድ፡ እንዝዝላ (እንደ ቀንበር በትከሻው የሚነትተው)።

ጅንፎ (ዥንፎ) ስ በትር እንዳይሰነጠቅ በብትሩ ቂጥ ላይ የሚሰካ ከብረት የሚሰራ ጥምዝ ቀለበት።

ጅዋጅዌ (ዥዋዥዌ) ስ ግራና ቀኝ በተተከሉ የእንጨት ወይም የብረት ምሰሶዎች አናት ላይ ከተጋደመ እንጨት ወይም ብረት ጋር በገመድ ታስሮ በተንጠለጠለ መቀመጫ ላይ ተቀምጠው ወደፊትና ወደኋላ በአየር ላይ በመወርወር ልጆች የሚጫወቱበት መጫወቻ፤ ጨዋታውም ጅዋጅዌ ይባላል።

ጅዋጅዌ

ጅው (ዥው)

ጅው አለ ግ ሄደ።

ጅው ብሎ ሄደ 1. ምንም ሳያቆመው፣ ሳያግደው ነጎደ። 2. ወደግራ ወይም ወደቀኝ ሳይመራ ወይም ሳይቆም ቀጥ ብሎ ሄደ።

ጅው አለበት ራሱን አዞረው።

ጅው ያለ ቀጥ ያለ (መንገድ፣ ገደል፣ ...)።

ጅው ያለ ገደል ጥልቀት ያለው ቀጥ ያለ ገደል።

ጅው አደረገ ግ በአንድ ጊዜ ጭልጥ አድርጎ ጠጣ።

ጅጊ (ጅጌ) ስ የያንዳንዱን ሰው ስራ በየተራው በቡድን እየሆነ ለማከናወን፣ ለማካሄድ በስምምነት የሚፈጠር ጊዜያዊ የስራ ህብረት፣ ደቦ፡ ወበራ።

ጅግራ(ዥግራ) ስ ስጋው የሚበላ፡ በዱር የሚገኝ እንደዶሮ ወይም እንደቆቅ ያለ ዥንጉርጉር የአሞራ ወገን(ስእሉን አሞራ ስር ተመ.)።

ጆ የ "ጀ" ፊደል ሳብእ ዘር።

ጆሮ ስ 1. ለመስማት ወይም ለማዳመጥ የሚያገለግል የሰውነት ክፍል(ስእሉን ራስ ስር ተመ.)። 2. የሲኒ፡ የኩባያ የእንስራ፡... መያዣ።

ጆሮ ዳባ ልበስ አለ ሰምቶ እንዳልሰማ ሆነ።

ጆሮውን ሰጠ 1. ሆን ብሎ አዳመጠ። 2. ሰምቶ ተቀበለ፣ አመነ።

ጆሮውን ተከለ አንድ ነገር ለመስማት፣ ለማዳመጥ አቆበቆበ፣ ጣረ።

ጆሮውን ቀሰረ ለማዳመጥ ተዘጋጀ፡ ጓጓ፡ ፈለገ።

ጆሮውን ጣለ 1. ለማዳመጥ አቆበቆበ፡

ጆሮውን ዝግጁ አደረገ:: 2. በህመም ምክንያት ጆሮውን ወደታች አንጠለጠለ፤ አንዘለዘለ (ለምሳሌ ውሻ)::

ጆሮዬ ገማ በየጊዜው የምሰማው መጥፎ ነገር በዛ፤ ሰለቸኝ::

ጆሮ ለጆሮ ቅርብ ለቅርብ::

ጆሮ የሚጠልዝ ጆሮን የሚያሳምም፣ የሚያደነቁር ከፍተኛ ድምፅ::

የጆሮ ልም/ቅጠል ስ ቀለበትን፣ ጉትቻን፣ ሎቲን ለማንጠልጠያ እንዲሆን የሚበሳው፣ ከወደታች ያለው የጆሮ ጫፍ(ስእሉን ራስ ስር ተመ.)::

የጆሮ ታምቡር ስ በጆሮ ውስጠኛ ክፍል የሚገኝ፣ የድምፅ ሞገድ ሲያርፍበት የሚርገበገብ ስስ ነገር ወይም አካል::

የጆሮ ወርቅ ስ ከወርቅ የተሰራና በጆሮ ላይ የሚንጠለጠል ጌጥ::

ጆሮ ደግፍ ስ ከጆሮ በታች የሚገኙ እጢዎችን የሚያሳብጥ በሽታ::

ጆሮ ግንድ ስ በጆሮ አካባቢ ያለ የሰውነት ክፍል::

ጆሮ ግንዱን አለው 1. ከጆሮው አካባቢ መታው:: 2. ሸጠው:: 3. አታለለው::

ጆሮጠቢ ስ ወሬ እየለቃቀመ የሚያቀብል፤ ሰላይ::

ጆተሬ "ጎተሬ"ን ተመ.

ጆተኒ (ጆቶኒ) ስ የእግር ኳስ ሜዳና የተጫዋቾች ምስል ያለበትን ቅርፅ ከነእጀታዎቹ እንዲይዝ ተደርጎ በጠረጴዛ መልክ የተሰራ የኳስ መጫወቻ፤ ጨዋታውም ጆተኒ ይባላል::

ጆፌ ስ ጆፍጃፋ፤ ፀጉሩ ወይም ላባው፣... ብዙ የሆነ::

ጆፌውን ጣለ በአንድ ነገር ዙሪያ ወይም አካባቢ አንዣበበ::

ጆፌ አሞራ ስ ላባው ብዙ የሆነ ትልቅ አሞራ፤ ጥንብ አንሳ (ስእሉን አሞራ ስር ተመ.)::

ጆፍጆፌ ስ ብዛትና ርዝመት ያለው ፀጉር::

ጇ ስ የ "ጇ" ፊደል ፍንፅቅ ዘር::

ገ

ገ ከ"ጀ" ፊደል ዘር ቀጥሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል (ግእዙ ሆሄ)።

ገሃ ስ 1. ጠንካራነት የሌለው፤ በቀላሉ ፍርክስክስ የሚልና እርጥበት ቶሎ የሚለየው የአፈር አይነት። 2. በፍም የሚበስል ብርኩታ፤ ቂጣ።

ገሃነም ስ ሃጢአት የሰራ ወይም በደል የፈፀመ ሰው ከሞት በሗላ ቅጣት ይቀበልበታል ተብሎ በሃይማኖት ሰዎች ዘንድ የሚታመንበት የስቃይና የፍዳ ቦታ።

ገሃነመ እሳት ዝ.ከ.

ገሃድ ስ 1. ስውር ያልሆነ፤ ግልፅ ወይም ይፋ። 2. "ጋድ"ን ተመ.

***ገለለ**

ገለልተኛ ቅ 1. በሰው ነገር ጣልቃ የማይገባ። 2. ከሌላው ነጠል ወይም ራቅ ብሎ ያለ።

ገለልተኛ አገሮች ስ ሃያላን ተብለው ከሚታወቁት አገሮች ጋር ከየትኛውም ያልወገኑ ወይም የእነሱ ተባባሪ ያልሆኑ አገሮች።

ግላሎ (ገላሎ፥ጋለሎ) ስ ከእርሻና ከአዝርእት መሃል ተነቅሎ ወደ ውጭ የሚጣል አረም።

ግል በፊደል ተራው ተመ.

ተገለለ ግ ተለየ፥ ተነጠለ፤ ራቀ፤ ብቸኛ ሆነ።

አገለለ ግ ለየ፤ ነጠለ፥ አራቀ፥ ለብቻ አደረገ።

ገለመጠ "ገላመጠ"ን ተመ.

ገለማ ግ 1. ብዙ ከመመገብ የተነሳ አንገፈገፈ(ብዙ ጊዜ ጣፋጭ ነገር)። 2. ጣእሙ ወይም ሽታው ተበላሸ (ብዙውን ጊዜ ምግብ)።

ገለሞተ

ገለሞተች ግ ጋለሞታ ሆነች።

ጋለሞታ ስ 1. እድሜዋ ለትዳር ደርሶ ያላገባችና ብቻዋን የምትኖር ሴት። 2. ባል አግብታ የሞተባትና ብቻዋን የምትኖር ሴት። 3. ሸርሙጣ፤ አመንዝራ ሴት። 4. ባል ፈታ ብቻዋን የምትኖር ሴት።

ግለሙትና ስ 1. የብቸኝነት ኑሮ (ለሴት) 2. የዘሙት ኑሮ፥ሸርሙጥና ።

አገለሞተ ግ ከባልዋ የተፋታች ሴትን አስጠጋ ወይም ረዳ።

***ገለሰለሰ**

ገለስላሳ ቅ ክፍል ክፍል ብሎና ተዘናፍሎ የሚታይ (የጤፍ ዛላ፤ ሳር፤ ፀጉር)።

ተግለሰለሰ ግ ክፍል ክፍል ብሎ ተዘናፈለ ወይም ተኛ (የጤፍ ዛላ፤ ፀጉር፥...)።

አግለሰለሰ ግ ክፍል ክፍል ብሎ እንዲዘናፈል ወይም እንዲተኛ አደረገ (የጤፍ ዛላን፥ ፀጉርን፥...)።

ገለሰሰ ግ 1. ገለፈጠ ወይም ድድን አሳየ። 2. (ሰው ወይም ነፋስ) ዛፍን ከስር ነቅሎ ጣለ፤ ገረሰሰ፥ ገነደሰ።

ተገለሰሰ ግ ተገረሰሰ፤ ተገነደሰ (ዛፍ)።

ገለበ^1 ግ እንደ ቀሚስ ያለ ልብስን በመግለጥ ወይም በመገፈፍ እርቃንን አሳየ፤ ራቁት አደረገ።

ተገለበ ግ ተገለጠ፤ እርቃኑን ቀረ፤ ተራቆተ።

ገለበ^2 ግ ላይ ላዩን ብቻ አቀጠለ፥ አሳረረ(እሳት)። *ላሸሮውን እሳት ገለበው።*

ግልብ ቅ 1. በደንብ ያልበሰለ ወይም ላይ ላዩን ብቻ እሳት ያገኘው።2. (ዘይ.) ሀ. በጠለቀ እውቀት ላይ ያልተመሰረተ ወይም በደንብ ጥናት ያልተደረገበት፤ ብስለት የሌለው። *የቀረበው ሃሳብ ግልብ ነው።* ለ. የጠለቀ እውቀት የሌለው፥ ጥራዝ ነጠቅ (ሰው)።

ተገለበ ግ ላይ ላዩን ተቃጠለ ወይም አረረ።

***ገለበለበ**

ግልብልብ ቅ በፍጥነት ቶሎ ቶሎ የሚነድ ወይም የሚቃጠል (እንደሳርና ገለባ ያለ ነገር)።

ተግለበለበ ግ በፍጥነት ቶሎ ቶሎ ነደደ፥ ተንቀለቀለ፥ ተንበለበለ።

አግለበለበ ግ በፍጥነት ቶሎ ቶሎ አንቀለቀለ፥ አነደደ፥ አንበለበለ።

ገለበጠ ግ 1. አንድን ነገር ከአንድ እቃ ወደ ሌላ እቃ አዛወረ። 2. አጋባ፤ ባዶ አደረገ።3. ደፋ፤ ከነበለ። 4. በብዛት ጠጣ ወይም ከለበሰ። 5. ለወጠ፥ ቀየረ (ፍርድን፥ ሃሳብን፡. . .)። 6. የውስጡን ወደ ውጭ ወይም የታቹን ወደ ላይ በኩል አደረገ።7 አንድን ፅሁፍ ከሌላ ፅሁፍ ላይ እየወሰደ ፃፈ ወይም ቀዳ። 8. ከአንድ ቋንቋ ወደ ሌላ ተረጎመ ። 9. በሃይል ስልጣን ነጠቀ ወይም ወሰደ። *የዘውድ አገዛዙን የገለበጠው ወታደር ነው።*

ገልብጥ ቅ (ስድብ) ጠጪ፥ ቀምቃሚ።

ገልባጣ 1. በአንድ አሳብ የማይረጋ፥ አቋም የለሽ፥ ወላዋይ። 2. ቅርፁ እንደ ሰፌድ ወይም ገርግ ሰሃን ያለ ሆኖ ከስረኛው ወይም ከታችኛው ክፍል ወደላይ የተለመጠ፥ ገሳሳ (እቃ)።

ገልባጭ ቅ ገልብጥ።

ገልባጭ መኪና እንደ አፈር፥ አሸዋ፥ ድንጋይ ያሉትን ነገሮች ተጭኖ ሌላ ቦታ በመውሰድ ያለ ሰው ጉልበት በራሱ ሃይል ማራገፍ የሚችል መኪና።

ግልባጭ ስ ቅጅ፥ ኮፒ (የፅሁፍ)።

ግልብጥ ቅ 1. የውስጠኛው ክፍል ወደላይ የሆነ ወይም የተገለበጠ። 2. ወላዋይ፥ በሃሳቡ የማይረጋ፥ የቀድሞ ሃሳቡን ለውጦ ተቃራኒውን የያዘ። ስ 3. አሰራሩ ወደ ውጭ የሆነ ጉንጉን፥ የሹሩባ አይነት።

ተገለበጠ ግ 1.ተደፋ፥ ተከነበለ። 2.የውስጠኛው ወይም የታችኛው ክፍል ወደ ውጭኛው ወይም ወደላይኛው በኩል ሆነ።3. ተለወጠ፥ ተቀየረ (በፊት ከነበረው አስተሳሰቡ፥ እምነቱ፥...)። 4. በሃይል ከስልጣኑ ተወገደ ወይም ወረደ። 5. ተተረጎመ፥ ተወሰደ። *ይህ ቃል ከእንግሊዘኛ የተገለበጠ ነው።* 6. ከሌላው ነገር ላይ ተቀዳ፥ ተፃፈ።

ተገለባበጠ ግ 1. ተተረማመሰ፥ ተመሰቃቀለ። 2. ተቀያየረ፥ ተለዋወጠ (ሃሳብ፥ ውሳኔ፥...)። 3. በፊት የነበረው ሃሳቡ፥ ውሳኔው፥ አቋሙ ተለወጠ ወይም ተቀየረ።

ተገለባባጭ ቅ ሃሳቡን የሚቀያይር፥ ወላዋይ፥ በአንድ አቋም የማይፀና።

ተገላበጠ ግ 1. ከነበረበት ከአንደኛው ወገን፥ አቅጣጫ ወይም ጎን ወደ ሌላው ወገን ወይም አቅጣጫ ዞረ። 2. በመግዛትና በመሸጥ ሂደት ላይ ገንዘቡ ተንቀሳቀሰ። 3. ከመወፈር የተነሳ ከወደመቀመጫ በኩል ያለ የሰውነት ክፍል በመራመድ ጊዜ ጎልቶ በሚታይ ሁኔታ ተንቀሳቀሰ።

አገለባበጠ ግ 1. አተረማመሰ፥ አመሰቃቀለ። 2. ቀያየረ፥ ለዋወጠ። 3. ሸቀጥን በመግዛትና በመሸጥ ገንዘብን አንቀሳቀሰ።

አገላበጠ ግ 1. አለዋወጠ፥ አቀያየረ፥ አዘዋወረ። 2. ሸቀጥን በመግዛትና በመሸጥ ገንዘብ አንቀሳቀሰ። 3. መታ፥ አንቆራጠጠ (በዱላ)። 4. እየገለጠ አየ (መፅሃፍን፥ መፅሄትን፥...)።

አስገለበጠ ግ እራሱ የፃፈውን ወይም የሰራውን ሌላ ሰው እንዲቀዳ፥ እንዲፅፍ ፈቀደ፤ አስኮረጀ።

ገለባ ስ 1. የተበነባበረ የገብስ፥ የስንዴ፥... አገዳ ወይም የብርእ ድቃቂ። 2. የእህል አሰር፥ ንፍሽ፥ እንግውላይ። 3. (ዘይ.) ቀላል፥ ፍሬቢስ ቁም ነገር የሌለው።

*ገለታ

ግልቱ ቅ ከርታታ፥ ባካና፥ ባተሌ።

ተንገላታ ግ ተጉላላ፥ ተንከራተተ።

አንገላታ ግ አጉላላ፥ አንከራተተ።

ገለታ ስ ወሮታ፥ ውለታ፥ ብድራት።

*ገለወደ

ገልዋዳ ቅ (ስድብ) ስራ ፈቶ ወዲያ ወዲህ የሚል፥ አውደልዳይ።

ተንገላወደ ግ ስራ ፈቶ ወዲያ ወዲህ አለ፥ዞረ።

አንገላወደ ግ ስራ አስፈታ፥ ወዲያና ወዲህ አንቀዋለለ።

*ገለደመ

ግልድም ስ ከወገብ በታች ሰውነት ላይ ተጠምጥሞ የሚለበስ ብትን ወይም ዝርግ ጨርቅ፥ሸርጥ።

ግልድምሽ ዝ.ከ.

ተገለደመ ግ በወገብ ላይ ታሰረ፥ ተሸረጠ (ያልተሰፋ ብትን ጨርቅ፥ ሸርጥ)።

አገለደመ ግ አሸረጠ፤ ከወገቡ በታች ሰውነቱ ላይ በመጠምጠም ያልተሰፋ ጨርቅን ወይም ግልድምን ለበሰ።

ገለዶ ስ ቅርፀ ደጋን የበግ ፀጉር መሸለቻ ቢላዋ።

*ገለጀጀ

ገልጃጃ (ገለጀጅ) ቅ (ስድብ) ቂል፥ ሞኝ፥ ነሁላላ፥ጅል።

ተንገላጀጀ (ተንገለጀጀ) ግ ተጃጃለ፥ ሞኝ ሆነ፥ ቄለ።

አንገላጀጀ (አንገለጀጀ) ግ አጃጃለ፥ አቄለ፥ ሞኝ አደረገ።

*ገለገለ

ግልጋሎት ስ ጥቅም፥ስራ።

ተገለገለ ግ ለአንድ አይነት ተግባር ተጠቀመ። *በባንኩ የተገለገለው ብዙ ሰው ነው / መኪናውን ለስራ ብቻ ተገለገለበት።*

ተገልጋይ ቅ ተጠቃሚ ።

አገለገለ ግ 1. ጥቅም ሰጠ ወይም ጥቅም ላይ ዋለ። 2. ተቀጣሪ በመሆን ወይም በሌላ መልክ ስራ ሰራ፤ የጉልበት፥ የእውቀት አገልግሎት አበረከተ።

አገልጋይ ቅ ተቀጥሮ የሚያገለግል (ብዙውን ጊዜ በግለሰብ ቤት ውስጥ)።

አገልግሎት ስ ጥቅም፥ ስራ።

ከአገልግሎት ውጭ ነው አርጅቷል ወይም ተበላሽቷል፥ ጥቅም አይሰጥም።

የአገልግሎት አንድ ሰው ለተሰጠው ግልጋሎት የሚከፍለው ተጨማሪ ክፍያ ወይም አንድ ሰው ለሰጠው አገልግሎት የሚከፈለው ተጨማሪ ክፍያ።

የአገልግሎት ካሳ ስ አንድ ሰው ተቀጥሮ ካገለገለበት መስሪያ ቤት ሲለቅ ወይም መስሪያ ቤቱ ሲፈርስ መስሪያ ቤቱ የሚሰጠው ገንዘብ ።

የአገልግሎት ዘመን አንድ ሰው ወይም ነገር የሰራበት ወይም የሚሰራበት፥ ጥቅም የሰጠበት ወይም የሚሰጥበት ጊዜ።

ገለጠ (ገለፀ) ግ 1. ገፈፈ፥ ገለበ፥ ከፈተ (ልብስን፥መጋረጃን፥የተሸፈነን፥የተከናነበን ነገር)።

2. ወለል አለ፥ ብርሃን ሆነ፤ ጠራ፤ ለቀቀ፡፡ *ጨለማው ገለጠ፡፡* 3. ምስጢርን በይፋ አወጣ፥ ተናገረ ወይም አወራ፡፡ 4. አስረዳ፥ አብራራ፥ አፍታታ፥ ግልፅ አደረገ፡፡

መግለጫ ስ 1. ስለአንድ ጉዳይ በፅሁፍ ወይም በቃል የሚቀርብ ማብራሪያ፡፡ 2. አንድ ምልክት ስለሚወክለው ሃሳብ ማብራሪያ ሆኖ የሚያገለግል ፅሁፍ፡፡

ገለፃ(ገለጣ) ስ ማብራሪያ፥ መግለጫ ፡፡

ገላጣ ቅ ሜዳ፥ መስክ ወይም በላዩ ላይ የተሰራ ወይም የበቀለ ነገር የሌለበት፥ በምንም ነገር ያልተሸፈነ (ባዶ መሬት)፡፡

ግላጭ (ብዙ ጊዜ ከ "በ" ጋር ይነገራል) ስ 1. ያለምንም ተሸማቂ፥ ለብቻ፡፡ *የሚፈልገውን በግላጭ ላገኘው፡፡* 2. ዝናብ ወይም ደመና የሌለው፥ ብሩ (ቀን፥ ሰማይ)፡፡

ግልፅ (ግልጥ) ቅ 1. ገሃድ፥ ይፋ፡፡ 2. ሽፍን ወይም ድፍን ያልሆነ፡፡ *ግልፅ መኪና፡፡* 3. የተብራራ፥ ቀላል፥ ውስብስብ ያልሆነ (ሃሳብ፥ ፅሁፍ፥…)፡፡

ተገለጠ ግ 1. ተገፈፈ፥ ታየ፥ተከፈተ (የተሸፈነ ነገር)፡፡ 2. ይፋ ወጣ፥ ተነገረ ወይም ተወራ (ምስጢር)፡፡ 3. ግልፅ ሆነ፥ ታወቀ፥ታየ፡፡

ተጋለጠ ግ 1. የፈፀመው ድርጊት ይፋ ወጣ፥ ታወቀበት፡፡ 2. ለአደጋ፥ለአፍረት፥… ተዳረገ፥ ተጋፈጠ፡፡ 3. ችግር ወይም አደጋ ሊደርስበት ሆነ፤ ለአደጋ ወይም ለችግር ተመቻቸ፡፡

አጋለጠ ግ 1. አሳልፎ ሰጠ፥ ወነጀለ (ምስጢር በማውጣት)፡፡ 2. አንድን ነገር አብሮ ለማድረግ ከተስማማ በኋላ ሃሳቡን ለውጦ አፈገፈገ፥ አጋፈጠ፡፡

ገለጠመ ግ 1. ሰበረ፥ ቀለጠመ፥ አነከተ፡፡ 2. ገረሰሰ፥ ገነደሰ፥ ጣለ(ዛፍን)፡፡ 3. (ዘይ.) ናቀ፥ ሰደበ፥ አዋረደ፡፡

ገለጠጠ ግ በለጠጠ፥ በጣም ገለጠ፡፡

መገለጢጥ ቅ (ስድብ) በሆነው ባልሆነው የሚስቅ፥ ገልፋጣ፡፡

ገልጣጣ (ገለጠጥ) ቅ መገለጢጥ፡፡

ተገለጠጠ ግ ተበለጠጠ፥ በጣም ተገለጠ፡፡

ተንገለጠጠ ግ ተገለጠጠ፡፡

አንገለጠጠ ግ ገለጠጠ፡፡

ገለፀ "ገለጠ"ን ተመ.

ገለፃ "ገለጠ" ስር ተመ.

ገለፈት ስ 1. ቅርፊት፥ ልጣጭ፥ ሽፋን (የጥራጥሬ፥…)፡፡ 2. የእባብ ቆዳ ግልፋፊ፡፡

ገለፈጠ ግ 1. በሆነ ባልሆነው ነገር ሳቀ፥ ድዱን ገለጠ፡፡ 2. ሳጠ፥ ገለፈፈ፡፡

ገልፋጣ (ገለፈጥ) ቅ (ስድብ) በሆን ባልሆነ ነገር የሚስቅ፥ መገለጢጥ፡፡

ግልፍጥ ዝ. ከ.

ተገለፈጠ ግ ተሳጠ፥ ተገለፈፈ፡፡

ገለፈፈ ግ ሳጠ፥ ገፈፈ (ገለፈትን፥ ቆዳን)፡፡

ገለፈፍ (ገልፋፋ) ቅ ሞኝ፥ ጅል፥ ቂል፡፡

ግለፋፊ ስ ልጣጭ፥ ቅርፊት፡፡

ግልፍፍ ቅ ገለፈፍ፡፡

ተገለፈፈ ግ ተሳጠ፥ ተነሳ (ቆዳ፥ ቅርፊት፥..)፡፡

ገላ ስ ከላይ የሚታየው ሰውነት ወይም አካል፡፡

ገላው ነውር አወጣ ገላው አበጠ ወይም ቆሰለ ወይም ለምፅ ወጣበት፡፡

ገላውን ሰደደ አረፈ፥ ፍርሃት አልባ ሆኖ ያለ ስራ ወይም ያለ ስጋት ተቀመጠ፡፡

የገላ ሳሙና ስ በተለይ ለሰውነት መታጠቢያ የተሰራ ሳሙና፡፡

ገላ ነክ ስ ከውስጥ የሚለበስና በቀጥታ ገላ ላይ የሚያርፍ (ውስጥ ልብስ፥ ሙታንታ)፡፡

ገላሎ "*ገለለ" ስር "**ግላሎ**"ን ተመ.

ገላመጠ (ገለመጠ) ግ 1. በግልምጫ አይን ተመለከተ፡፡ 2. አቃጠለ፥ ፈጀ(የእሳት ወላፈን)፡፡

ግልምጫ ስ የጥላቻ፥ የንቀት፥ የቁጣ አስተያየት፡፡

ተገላመጠ ግ 1. ወደ ኋላ ወይም ግራና ቀኝ ዞር ዞር እያለ አየ፡፡ 2. ገላመጠ፡፡

ገላገለ ግ 1.ለያየ ወይም አስጣለ፥ ከለከለ (እየተደባደቡ ወይም እየተጣሉ ያሉ ሰዎችን)፡፡ 2. አስታረቀ፥ አስማማ፡፡ 3. ከችግር፥ ከመከራ፥… አሳረፈ፥ አላቀቀ፡፡

ገላጋይ ቅ ተው ባይ፥አስታራቂ፡፡

ገላጋሊ ቅ የሚያረካ፥ የሚያስደስት፥ አንጀት አርስ፡፡

ግልግል ስ 1. እፎይታ፥ እረፍት፡፡ 2. እርቅ፥ ሽምግልና፡፡

ተገለገለ ግ ልማታ ወይም ልደባደብ አለ፥ ተጋበዘ፡፡

ተገላገለ ግ 1. ከችግር፥ ከበሽታ፥ ከጭንቀት፥… ተላቀቀ፥ አረፈ፡፡ 2. ታረቀ፥ ተስማማ፡፡

ተገላገለች ግ ወለደች፡፡

አገላገለ ግ 1. አለያየ፥ ከለከለ፥ አስተወ፥ ገላገለ (እየተደባደቡ ወይም እየተጣሉ ያሉ ሰዎችን)፡፡ 2. አዋለደ፡፡

ገላጣ "ገለጠ" ስር ተመ.

ገል ስ በአብዛኛው ለእሳት መጫሪያ የሚያገለግል

የሸክላ እቃ ሰባሪ።

ገልባጭ "ገለበጠ" ስር ተመ.

ገልብጥ ዝ. ክ.

ገልቱ ቅ (ስድብ) ሙያ ቢስ፥ ረሀጥ።

ገልዋዳ "ገለወደ" ስር ተመ.

ገልጃጃ "*ገለጀጀ" ስር ተመ.

ገልጣጣ "ገለጠጠ" ስር ተመ.

ገልፋጣ "ገለፈጠ" ስር ተመ.

ገልፋፋ "ገለፈፈ" ስር ተመ.

ገመለ ግ 1. በወፍራሙ የተቦካን የማሽላ ወይም የበቆሎ ሊጥ በወፍራሙ ጋግሮ ሳይበስል አወጣ። 2. ወፍራምና የማያምር እንጀራ ጋገረ።

ግምል ስ 1. ሳይበስል የወጣ ዳቦ ወይም ቂጣ። ቅ 2. (ዘይ.)ከተቀመጠበት የማይነሳ፥ ውዝፍ፥ ሰነፍ።

ተገመለ ግ ተጋግሮ ሳይበስል ወጣ (ቂጣ፥ዳቦ፥...)።

ገመመ ግ ሰበረ ወይም ጎረደ (የሸክላ እቃ አንገቱን)።

ገማሞ ቅ አንገቱ የተሰበረ ወይም የተሸረፈ (እንስራ፥ ገንቦ፥...)።

ገማሞ ራስ ስ (ስድብ) ትልቅና ሞላላ የሆነ ራስ።

ገሙምተኛ "*ጉገመ" ስር ተመ.

ገመረ ግ አደገ፥ ተለቀ፥ ከፍ አለ።

ገመሬ [ዝንጀሮ] ስ ትልቅ አውራ ዝንጀሮ።

ገመሮ "ጉመሮ"ን ተመ.

ገመሰ ግ 1. ሁለት ቦታ ከፈለ፥ ሁለት አደረገ። 2. አረሰ፥ሰነጠቀ(መሬትን)። 3. ፈነከተ፥ ተረተረ።

ገሚስ ቅ ግማሽ ወይም እኩሌታ።

ግማሽ ቅ አንድ ሁለተኛ ወይም የአንድ ነገር እኩሌታ።

ግማሽ ቀን ስ ከሰአት በፊት ወይም ከሰአት በሗላ ያለው ቀን።

ተጋመሰ ግ 1. እኩል ተጋራ ወይም ተካፈለ። 2. ግማሽ ላይ ደረሰ፥ ሊያልቅ ተቃረበ።

ተጋማሽ ቅ ግማሽ ወይም እኩሌታ።

አጋመሰ ግ 1. አካፈለ ወይም አጋራ። 2. ግማሽ ላይ አደረሰ ወይም ሊጨርስ ተቃረበ።

አጋማሽ ቅ ግማሽ ወይም እኩሌታ።

***ገመሸረ**

ተገማሸረ ግ 1. አሟረበት፥ ተዘናፈለ፥ ዳበረ (ሰብል፥ ሳር፥...)። 2. (ዘይ.) የኩራት አካሄድ ሄደ፥ ተጎማለለ።

አገማሸረ ግ አሳመረ፥ አዘናፈለ፥ አዳበረ (ሰብልን፥ ሳርን፥...)።

ገመተ ግ 1. በአይን ሀሊና መዘነ ወይም ገመገመ። 2. ይሆናል ብሎ አሰበ።

ገማች ቅ ዋጋ የሚተምን።

ግምት ስ 1. የአንድ ነገር (የመጠን ወይም የልክ) ተመን። 2 ትክክለኛው መጠን፥ ልክ ወይም ሁኔታ ሳይታወቅ በይሆናል እንዲህ ነው ተብሎ የሚሰጥ አስተያየት።

ተገመተ ግ 1. በይሆናል ተመዘነ፥ ተለካ፥ ተገመገመ። 2. በሰራው፥ በተናገረው፥... ተመዘነ፥ ተገመገመ፤ ትዝብት ላይ ወደቀ።

ተገማመተ ግ እርስ በርስ ተፈታተኑ፥ ተሞካከሩ (በጉልበት፥ በጠባይ)።

አገማመተ ግ አስተዛዘበ።

አስገመተ ግ ትዝብት ላይ ጣለ።

ገመነ ግ ተናደደ፥ በገነ።

ተግመነመነ ዝ. ክ.

ገመና ስ 1. እንዳይታወቅ ወይም እንዳይገለጥ የሚፈለግ ነውር፥ ድክመት፥ እንከን። 2. ሌላ ሰው እንዲያውቀው የማይፈለግ የራስ ችግር ወይም የግል ሁኔታ።

ገመና ከታች ነውርን ወይም ምስጢርን የሚደብቅ ወይም የሚጠብቅ።

ገመደ ግ ሸረበ፥ አጠላለፈ (ክርን፥ገመድን፥...)።

ገመድ ስ ከፈትል ወይም ከልጥ ወይም ከቃጫ፥... እየተሸረበና እየተጠላለፈ የሚሰራና ለማሰሪያ፥ ለማንጠልጠያ፥.. የሚያገለግል ነገር።



ገመድ

በገመዱ ገባ አንዱ በሰራው ወንጀል ወይም ነገር ሌላው ተቀጣ፤ ታሰረ።

[የ]ገመድ ዝላይ ስ ጫፍና ጫፉን ተይዞ በጭንቅላት ላይና በእግር ስር የሚዞርን ገመድ በተደጋጋሚ በመዝለል የሚደረግ ጨዋታ።

ገመድ አፍ (ስድብ) ተብታባ፥ ኮልታፋ (ለአዋቂ)።

ገመድ ጉተታ ስ ቁጥራቸው የተመጣጠነ ሁለት ቡድኖች ከወዲያና ከወዲህ የገመዱን ጫፎች ይዘው በመጎተት አንደኛው ወገን ሌላውን ከተወሰነ ክልል ውስጥ ጎትቶ ለማስገባትና አሸናፊ ለመሆን የሚደረግ የውድድር ጨዋታ።

ገመደለ ግ 1. በትልቁ ቆረሰ (ለምሳሌ ዳቦን)።

2. አዛባ፣ አጣመመ (ፍርድን)። 3. አራከሰ፣ ዝቅ አድርጎ ገመተ (ዋጋን)።

ገመድ "ገመደ" ስር ተመ.

ገመገመ ግ 1. ገመተ፣ ተመነ፣ በአይን ህሊና ለካ። 2. የአንድን ስራ ሁኔታ፣ ጥራት፣ አሰራር አጥንቶ ወይም አይቶና መዝኖ አስተያየት ሰጠ፣ ድክመትና ጥንካሬውን አሳየ።

ገምጋሚ ቅ የአንድን ነገር ጥራት፣ ዋጋ፣ ... ወይም የአንድን ስራ ሁኔታ ወይም ክንውን፣... አይቶ ወይም አጥንቶና መዝኖ አስተያየት የሚሰጥ።

ግምገማ ስ የአንድን ስራ ሁኔታ፣ ክንውን፣ ጥራት፣... የማየት ወይም የማጥናትና የመመዘን ተግባር።

***ገመገመ**

ተሰገመገመ ግ ዝናም ሲጥል ተቃረበ፣ ሰማዩ ተጉረመረመ፣ የነጎድጓድ ድምፅ ተሰማ።

አሰገመገመ ግ አጉረመረመ፣ የነጎድጓድ ድምፅ አሰማ (ሰማይ)።

ገመገም ስ የተራራ አግድመት፣ ተረተር።

ገመጠ ግ 1. በጥርሱ ቆርሶ በላ (ዳቦን፣ ፍራፍሬን፣...)። 2.ሸረፈ፣ ሰበረ (ለምሳሌ እንስራን፣...)።

ገማጣ ቅ ሸራፋ፣ ሰባራ፣ ገምጫ።

ተገመጠ ግ ተሸረፈ፣ ተሰበረ።

ገመጠጠ ግ አሽሟጠጠ፣ አንጓጠጠ።

ገምጣጭ ቅ አሽሟጣጭ፣ ነቃፊ ።

ገሚስ "ገመሰ" ስር ተመ.

ገማ ግ ከረፋ፣ ሸተተ፣ ጠነባ።

ግማት ስ መጥፎ ሽታ፣ ክርፋት።

ግማታም ቅ (ስድብ) መጥፎ ሽታ ያለው፣ ክርፋታም።

ግም ቅ 1.ቆሻሻ፣ ፅዳት የሌለው፣ መጥፎ ሽታ ያለው። 2. (ዘይ፣ ስድብ) ረሀጥ፣ ሙያ ቢስ፣ ዝርክርክ።

ተግማማ ግ ተበላሸ፣ ተበሳበሰ፣ ገማ።

አገማች ግ ሳትፈለፍል ቀረች፣ አበለበሰች (ዶሮዋ እንቁላሏን)።

አግመዶ በል ስ ስጋን እስከሚሸት አቆይቶ የሚበላ እንደ ነብር ያለ አውሬ።

አግማማ ግ 1. አበሰበሰ፣ አበላሸ፣ እንዲገማ አደረገ። 2 .(ዘይ.)አጥላላ፣ አበሻቀጠ፣ አራከሰ።

ገማች "ገመተ" ስር ተመ.

ገማጣ "ገመጠ" ስር ተመ.

ገምባሌ (ገንባሌ) ስ ከቁርጭምጭሚት አንስቶ እስከ ጉልበት ያለውን የእግር ክፍል የሚያለብስ ከቆዳ ወይም ከሹራብ የሚሰራ የቅልጥም መሸፈኛ ወይም መከለያ።



ገምባሌ

ገምቤሎ "ጋምቤሎ"ን ተመ.

ገምቦ "ገንቦ"ን ተመ.

ገምናና(ገምናኔ) ቅ 1. ኩሩ፣ ጅንን። 2. ጀግና፣ ጎበዝ።

ገምጋሚ "ገመገመ" ስር ተመ.

ገምጣጭ "ገመጠጠ" ስር ተመ.

ገሞራ ቅ ብርቱ፣ ሃይለኛ፣ ኀበዝ።

ገረመ[1] ግ 1. ጨመተ፣ ረጋ አለ። 2. ገራም ሆነ፣ ለመደ።

ገራም ቅ 1. ቅን፣ ርህሩህ፣ ገራገር። 2. ሃይለኛ ያልሆነ፣ አመሉ ለስላሳ (ከብት)።

ገረመ[2] ግ ደነቀ። *ወሬውን ለሰማ ገረመኝ።*

ግሩም ቅ 1. ቆንጆ፣ ጥሩ። 2. ድንቅ።

ተገረመ ግ ተደነቀ፣ እፁብ ድንቅ አለ።

አስገረመ ግ አስደነቀ፣ እፁብ ድንቅ አሰኘ።

አስገራሚ ቅ አስደናቂ።

ገረመመ ግ ገላመጠ፣ በቁጣ አይን አየ።

ገረመደ (ጎረመደ) 1. በትልቁ ቆረሰ፣ ገመሰ። 2. ምድርን ገለባበጠ፣ በረቀበ፣ አረሰ (በመድፍ በቦምብ፣...)።

ገረረ ግ 1. በጣም አቃጠለ፣ ከረረ (ፀሃይ)። 2. በጣም ጋለ፣ ሰማ፣ ጠበረረ (ምጣድ)። 3. ተንበለበለ፣ ነደደ(እሳት)። 4. በጣም ደረቀ፣ ቀረፈደ፣ ተንከፈረረ(ብዙውን ጊዜ ቆዳ)።

ገራራ ቅ የጋለ፣ የሚያቃጥል።

ገረሰሰ ግ ከስሩ ነቅሎ ጣለ፣ አፈረሰ። *ነፋስ ዛፉን ከስሩ ገርስሶ ጣለው ።*

ገረሸ

ግርሻ ስ አንድ በሽተኛ እንደ መሻል ካለው በሃላ እንደገና እንደ አዲስ የሚያመው የመጀመሪያው አይነት በሽታ።

አገረሸ ግ 1. ተሽሎ ወይም ለቆ የነበረ በሽታ እንደገና አመመ፣ ህመሙ ተመለሰ። 2. (ዘይ.) እንደገና ተነሳ ወይም ተጀመረ (ፀብ፣ ፍቅር፣...)።

***ገረበበ**

ገርባባ(ገረበብ) ቅ ግጥም፣ ልበት፣ ልክክ የማይል ወይም ያሳለ (ከዳን፣ መዝጊያ)።

ገርበብ አለ ግ ግጥም ሳይል ቀረ፣ በመጠኑ ከፈት አለ፣ መለስ አለ (ክዳን፣ በር)።

ገርበብ አደረገ ግ ግጥም ሳያደርግ ወይም ሳላ አድርጎ ከደነ ወይም ዘጋ፣ መለስ አደረገ።

ተንገረበበ ግ አልጠጋ ወይም ልክክ አልል አለ፣ ተንከረፈፈ፣ ገርባባ ሆነ።

አንገረበበ ግ ገርበብ አደረገ።

ገረንክ ስ መልኩ ቀላ ያለ አሸዋማ ሆኖ ጀርባው ላይ ደመቅ የሚል፣ ጉያውና ደረቱ እንዲሁም የአይኖቹ ዙሪያ ነጭ የሆነ መልክ ያለው፤ ደረቅ በሆኑ ቆላማ ስፍራዎች የሚኖር የዱር እንስሳ፤ ጉንፍቴም ይባላል (ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።

ገረንገሬ ስ 1. በወይና ደጋ የሚበቅልና ተንከሬ የሚለው የዛፍ አይነት። 2. ከገረንገሬ እንጨት የሚገኝ ሙጫ።

ገረኘ ግ እግር ከወርች አሰረ፣ ቀፈደደ።

ገረዘ(ገዘረ) ግ 1. የወንድን ብልት ልንቡጥ ወይም የወሸላን ሸፋን ቀነጠበ፣ ቆረጠ። 2. የረዘመ የተከለን ጫፍ ቆረጠ፣ አስተካከለ።

ግርዝ ቅ የተገረዘ።

ግርዘት(ግዝረት) ስ የወንድን ብልት ልንቡጥ ወይም የወሸላን ሸፋን የመቁረጥ ድርጊት።

ተገረዘ ግ ተቀነጠበ፣ ተቆረጠ(የወንድ ብልት ልንቡጥ ወይም ሸፋን ወይም ተክል)።

ገረዘዘ ግ ተጫጫነ፣ አሸነፈ፣ ጣለ(ለምሳሌ እንቅልፍ)።

ገረደ ግ ገረድ አደረገ።

ገረድ ስ በገንዘብ ተቀጥራ ሰው ቤት የምታገለግል ሴት፤ የቤት ሰራተኛ።

ግርድና ስ ገረድ ሆኖ ማገልገል።

ተገረደች ግ ገረድ ሆነች።

ገረደሰ ግ ገነደሰ።

ገረደፈ ግ ከካ፣ ሸረከተ(እህልን)።

ግርድፍ ቅ 1. ሽርክት፣ ክርትፍ፣ ያልደቀቀ። 2. (ዘይ.) ያልተብላላ፣ ያልበሰለ ወይም በደንብ ጥናት ያልተደረገበት (ሃሳብ፣ አስተያየት፣...)።

ገረድ "ገረደ" ስር ተመ.

ገረጀፈ ግ ያለእድሜው ሰውነቱ ግዙፍ ሆነ፣ ትልቅ ሰው መሰለ፤ አረጀ።

ግርጃፋ ቅ ያለእድሜው ሰውነቱ ግዙፍ የሆነና ያረጀ የሚመስል።

ገረገረ^1 ግ 1. ገረገራ ሰራ፤ በግድግዳ መልክ በአጠና አጠረ፣ ገደገደ። 2. እንቅፋት ሆነ፣ አሰናከለ፣ አከላከለ፤ አወከ።

ገረገራ ስ 1. በአጠና ወይም በፍልጥ የሚሰራ የቤተክርስቲያን አጥር። 2. በመስመር እንደ አጥር ሆኖ የተተከለ የቤተክርስቲያን አፀድ።

ግርጋሪ ቅ እንቅፋት የሚሆን፣ የሚያሰናክል፣ አዋኪ።

ገረገረ^2 ግ 1. በረገገ፣ ደነበረ (ከብት)። 2. አቆበቆበ ለመበርገግ ዳርዳር አለ።

ግርጋሪ ቅ ደንባሪ፣ ድንጉጥ።

አገረገረ ግ ለመበርገግ ወይም ለመደንበር አቆበቆበ፣ ጆሮውን ሸመጠጠ (ከብት)።

ገረገራ "ገረገረ^1" ስር ተመ.

*ገረገበ

ግርግብ አለ ግ 1. በመጠኑ በሰለ፣ ሾቀ (ባቄላ፣ አተር፣...) ። 2. ታገሰ ወይም በረድ አለ (ረሃብ፣ ንዴት፣ ቁጣ)።

ተንገረገበ ግ በመጠኑ ተቀቀለ ወይም በሰለ፤ ሾቀ (ባቄላ፣ አተር፣...)።

አንገረገበ ግ 1. በመጠኑ አበሰለ ወይም ቀቀለ፤ አሾቀ (ባቄላን፣ አተርን፣...)። 2. (ዘይ.) አጠቃ፣ አሸነፈ (ጠላትን)።

እንግርግብ ስ በመጠኑ የተቀቀለ (ባቄላ፣ አተር፣...)።

ገረገደ "ገደገደ"ን ተመ.

ገረጋንቲ ስ ጠጠር፣ ኮረት።

ገረጣ ግ 1. ነጣ፣ በሰለ፣ ለመሰብሰብ ደረሰ (ሰብል)። 2. ወዘና ወይም ደም ግባት አጣ፤ አመድማ ሆነ።

ገረፈ ግ 1. መታ፣ ሸነቆጠ (በአለንጋ፣ በአርጩሜ፣...)።2. ለበለበ፣ ለመጠጠ (የእሳት ወላፈን)። 3. ግድግዳን በአሸዋ፣ በደቃቅ ጠጠርና በሲሚንቶ ድብልቅ በሻካራው መረገ። 4. ወይፈንን ለእርሻ ገራ ወይም አሰለጠነ።

ግርፊያ ስ በአለንጋ ወይም በጅራፍ፣... የሚደረግ ምት።

ግርፋት ስ 1. ግርፊያ። 2. በተገረፈ ገላ ላይ የሚታይ ሰንበር፣ ቁስል። 3. ብዙውን ጊዜ በአፍ ውስጥና በአፍ አካባቢ እንደ እከክ ሽፍ ብሎ የሚወጣ ቁስል። 4. ምች ።

ግርፍ ስ 1. በተገረፈ ሰውነት ላይ የሚታይ ሰንበር፣ ቁስል። 2. እርሻ የተለማመደ ወይፈን። 3. አንድን ስራ፣ ሙያ ፣ እምነት ወይም አስተሳሰብ ከሌላ ሰው በመቅሰም ወይም በመማር በድርጊቱ ወይም በአስተሳሰቡ እንደአስተማሪው የሆነ ሰው። *የእገሌ ግርፍ*። ቅ 4. በአሸዋ፣ በደቃቅ ጠጠር፣ በሲሚንቶ በሻካራው የተመረገ (ግድግዳ)።

ገረፍ ገረፍ አደረገ ግ እልፍ እልፍ ወይም ላይ ላዩን ተመለከተ ወይም ተናገረ።

ተጋረፈው 1. በአፉ አካባቢ ወይም በአፉ ውስጥ እንደ እከክ ሽፍ የሚል ቁስል ወጣበት፣ አመመው2. ምች መታው።

ገራ^1 ግ ፈረስን፣ በቅሎን አሰለጠነ(እንዲጋለብ፤ እንዲሰግር)።

ግር ቅ የተገራ፣ የሰለጠነ (ፈረስ፣ በቅሎ)።

ተገራ ግ ተማረ፣ ሰለጠነ (ፈረስ፣ በቅሎ እንዲጋለብ፣እንዲሰግር)።

ገራ^2 ግ ለዘበ፥ ገር ሆነ፥ ቀለለ።

ገር ቅ 1. የዋህ፥ ቅን፥ ተንኮል የሌለበት። 2. ጠንካራ ያልሆነ፥ ልል።

ገራገር ቅ የዋህ ቅን፥ ተንኮል የሌለበት።

ገራራ "ገረረ" ስር ተመ.

ገራም "ገረመ^1 " ስር ተመ.

ገራገር "ገራ^2" ስር ተመ.

ገሬ ስ 1. ማሩ የተመጠጠ ባዶ የማር እንጀራ፤ ከፎ። 2. ገመምተኛ (ከወባ በሽታ)።

ገሬንጭ ስ ያበርበሬ የመጀመሪያው ምርት ወይም ዛላ ከተለቀመ በኋላ በማሳው ላይ ቆሞ የሚቀረው የበርበሬ ተክል፤ ተክሉ በድጋሚ የሚሰጠው ፍሬ ወይም ዛላም ገሬንጭ ይባላል።

ገር "ገራ^2 " ስር ተመ.

ገርባባ "ገረበበ" ስር ተመ.

ገርዳሳ ስ ፀጉርን ወደ ላይ ደግፎ እንዲይዝ ተደርጎ በራስ ዙሪያ የሚታሰር ሻሽ፤ ቀልቤ።

ገርዳሳ ሻሽ ዝ.ክ.

ገርጃፋ "ገረጀፈ" ስር ተመ.

ገርጋሪ^1 "ገረገረ^1 ስር ተመ.

ገርጋሪ^2 "ገረገረ^2 ስር ተመ.

ገርጌሶ ስ መንቆሩ ጠፍጠፍ ብሎ በጣም ረዥም የሆነ፥ ነጭ ወይም ቡላ መልክ ያለውና ሞቃታማ በሆነ አካባቢ በመንጋ የሚኖር ትልቅ የአሞራ አይነት(ስእሉን አሞራ ስር ተመ.)።

ገሰረ ግ በብዛት ጠጣ፤ ገሸረ።

ገሰሰ^1 ግ 1. ጣሰ፥ ተላለፈ፥ አፈረሰ(ህግን) ። 2. ሻረ፥ ለወጠ፥ ገሰበጠ (ፍርድን)። 3. አጠፋ፥ ወሰደ (ክብረ ንፅህናን)።

ገሰሰ^2 ግ ለቀቀ፥ ደበዘዘ፥ ደበሰ(ወርቅ)።

ገሰሰ^3 ግ ግሰን አረባ።

ግስ ስ (ሰዋ.) የአረፍተ ነገር መግቻ፤ ማሰሪያ አንቀፅ ወይም ቃል።

ተገሰሰ ግ ረባ (ግስ)።

ገሰበ ግ 1. ይህንንም ያንንም ሳይመርጥ በላ ወይም ጠጣ። 2. በብዛት ጠጣ፤ ገሰረ።

ገሰገሰ ግ 1. ቶሎ ቶሎ ተራመደ፥ ተጣደፈ ፥ ፈጠነ። 2. አደገ፥ ረዘመ፥ ትልቅ ሆነ (ለምሳሌ ተክል)። 3.ተሻሻለ፥አደገ(በእውቀት፥ በስልጣኔ፥...)።

ገሲጋሽ ቅ ፈጣን ሂያጅ።

ገሰፀ(ገሰጠ) ግ 1. ተቆጣ። 2. መከረ።

ግሳፄ ስ 1. ቁጣ። 2. ምክር።

ተገሰፀ ግ 1. ቁጣ ደረሰበት፥ ተቆጣ። 2.ተመከረ።

ተግሳፅ ስ 1. ቁጣ። 2. ምክር።

ገሳ ስ 1 ጠርዙ እንደ ሰደፍ ስለትና ስፋት ያለው በረግረግ ቦታ የሚበቅል የሳር አይነት። 2. ከገሳና ከቄጠማ የሚሰራ የእረኞች የዝናም ልብስ።

*ገሳ

ግሳት ስ 1. ከሆድ ውስጥ በአፍ በኩል የሚወጣ ጋዝ ወይም ብስና። 2. ከሆድ ውስጥ ጋዝ ወይም ብስና በአፍ በኩል ሲወጣ የሚሰማው ድምፅ።

ግሳታም ቅ (ስድብ) ብስናታም።

አገሳ ግ 1. ከሆዱ ውስጥ በአፉ በኩል ጋዝ ወይም ብስና አስወጣ። 2. አስገሳ። 3 ለማስፈራራት፥ ቁጣን ለመግለፅ፥... ከፍተኛ ድምፅ አሰማ (አንበሳ፥ በሬ፥...)።

አስገሳ ግ ከሆድ ውስጥ በአፍ በኩል ጋዝ ወይም ብስና እንዲወጣ ምክንያት ሆነ (ምግቡ፥ መጠጡ፥ ...)።

ገሲጋሽ "ገሰገሰ" ስር ተመ.

ገሶ ስ ደንጎራ፥ ረዘምና ቀጥ ያለ እጀታ ያለው መጥረቢያ መሰል የጉድጓድ መቆፈሪያ።

ገሸለጠ ግ 1. ሳበ፥ መለጠ፥ ገፈፈ(ሽፋንን፥ ቆዳን)። 2. ገረፈ። 3. ፋቀ ወይም መለጠ (የቁርበት ፀጉርን)። 4. ስጋን ከአጥንት ለየ፥ ሳጠ። 5. ፈጀ፥ ለበለበ፥ አቃጠለ(የፈላ ውሃ ወይም እሳት)። 6. መነተፈ፥ ወሰደ፥ በላ (ገንዘብን)። 7. (ዘይ.) አማ።

ግሽልጥ ቅ የተገሸለጠ፥ ምልጥልጥ፥የተሳጠ፥ መለመላውን የቀረ።

ተገሸለጠ ግ 1. ተሳጠ፥ ተገለፈፈ፥ ተገፈፈ(ሽፋን፥ ቆዳ፥...)። 2. ተመለጠ፥ ተነሳ (የቁርበት ፀጉር)። 3. ተሳጠ፥ ተለየ፥ ተላቀቀ(ስጋ ከአጥንት)።

ተገሸላለጠ ግ ተሳሳጠ፥ ተመላለጠ።

ገሸረ^1 ግ 1. በአንድ ቦታ ለረጅም ጊዜ እንዲቀመጥ አደረገ። 2. አቆየ፥ አዘገየ፥ አስቀመጠ (ለምሳሌ ስራን)።

ተገሸረ ግ በአንድ ቦታ ለረዥም ጊዜ ተቀመጠ።

ግሽር ስ የጋን ወይም የማድጋ ውሃ።

ገሸረ^2 ግ በብዛት ጠጣ።

*ገሸሸ

ገሸሽ አደረገ ግ ችላ አለ፥ ተወት አደረገ፥ አገለለ።

*ገሸገሸ

ግሽግሽ አለ ግ ተንገሸገሸ።

·**ግሽግሽ (እንግሽግሽ) አደረገ** ግ አንገሸገሸ።

ተንገሸገሸ ግ ተማረረ፥ ተሰላቸ፥ ተንገፈገፈ።

አንገሸገሸ ግ 1. አስመረረ፥አሰለቸ፤አንገፈገፈ።

2. መረረ፥ ጎፈነነ።

ገበሎ ስ ረዥም ጭራ፣ አራት እግርና ሻካራ ቆዳ ያለው፣ ከተሳቢ እንስሳት ወገን የሚመደብ አነስተኛ እንስሳ።

ገበረ ስ 1. ግብር ሰጠ፣ ከፈለ። 2. ለጥ ሰጥ አለ፥ እሚጌን ብሎ ተገዛ።

መገበሪያ ስ 1. ግብር ወይም አስራት የሚገበርበት ቦታ ወይም ገበሎ ጊዜ። 2. (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ለቁርባን ወይም ለመስዋእት እንዲሆን ለቤተክርስቲያን የሚሰጥ ነጭ ስንዴ።

የመገበሪያ ቁና ስ በአንዳንድ አካባቢዎች ገበሬው ለቤተክርስቲያን ወይም ለመንግስት የሚሰ ጠውን እህል የሚሰፍርበት ቁና።

ገባር ስ የራሱ የሆነ ርስት የሌለውና የሌላ ሰው ርስት እያረሰ ለባለመሬቱ ግብር ይከፍል የነበረ ገበሬ ወይም አራሽ።

ግብር ስ 1. ገቢ ያለው ዜጋ ሁሉ በተወሰነ ጊዜ እንደገቢው መጠን ለመንግስት የሚከፍለው የተወሰነ ገንዘብ። 2. በቤተ መንግስት ወይም በታላላቅ ባለስልጣናት ቤት ይደረግ የነበረ ግብዣ። 3. ቀደም ገበሬ ለሚያርሰው መሬት ለመንግስት፥ ለመልከኛ፥… በእህል፥ በገንዘብ፣ በከብት፥ በጉልበት ስራ፥… መልክ ያደርግ የነበረው ክፍያ።

ግብር ገባ በቤተመንግስት ወይም በታላላቅ ባለስልጣናት ቤት በሚደረገው ግብዣ ላይ ተጋባዥ ሆኖ ተገኘ።

ግብር አገባ አንድ ባለስልጣን ወይም ንጉስ ድግስ አዘጋጅቶ ብዙ ሰዎችን ጋበዘ።

የግብር ይውጣ የግዴለሽነት ወይም ከልብ ያልሆነ ድርጊት።

የግብር ስንዴ የ "መገበሪያ"ን ሁለተኛ ፍቺ ተመ.

ግብረ በላ በድሮ ጊዜ ደመወዝ ወይም ሌላ መተዳደሪያ የሌለውና በንጉስ፣ በመሳፍንት፥… ቤት እየተቀለበ የሚኖር (ሰው)።

ግብረ ጠል ቅ ለያዘው መሬት ለመንግስት ግብር ያልከፈለ።

አስገበረ ግ አንድን አካል በጦር ወይም በሃይል አሸንፎ እንዲገብርለት አደረገ።

*ገበረ^1

ምግባር ስ 1. ስራ፣ አድራጎት። 2. ባህርይ ወይም ጠባይ።

ምግባረ መልካም ቅ ጥሩ፥ የሚያስመሰግን ባህርይ ወይም ጠባይ ያለው።

ምግባረ ሰናይ ስ መልካም ስራ።

ገቢር[ግስ] ስ (ሰዋ.) ቀጥተኛ ተሳቢ የሚያስፈልገው የግስ አይነት፤ አድራጊ ግስ።

ገባሬ ሰናይ ስ 1. በጎ አድራጊ። 2. (ኢ.ኦ.ተ.ቤ) በስርአተ ቅዳሴ ጊዜ ቅዳሴን በመሪነት የሚቀድስ ዋናው መሪ ቄስ ወይም ዲያቆን።

ግብር ስ ስራ፤ አመል ጠባይ።

ግብረሃዋርያ ስ የክርስቶስ ሃዋርያት የሰሩትንና ያስተማሩትን ትምህርት የሚገልፅ የሃዲስ ኪዳን መፅሃፍ ክፍል፤ የሃዋርያት ስራ።

ግብረሰዶም ስ በወንድና በወንድ መካከል የሚደረግ የግብረስጋ ግንኙነት።

ግብረስጋ ስ ፍትወት፤ ሩካቤ ስጋ፤ ወሲብ።

ግብረአበር ስ በተንኮል ወይም በመጥፎ ስራ ተባባሪ ወይም አባሪ የሆነ፤ ሌረኛ።

ግብረገብ ስ 1. የጥሩ ወይም የመልካም ስራ ትምህርት። 2. መልካም ምግባር።

ተገብሮ [ግስ] ስ (ሰዋ.) ቀጥተኛ ተሳቢ የማያስፈልገው የግስ አይነት ወይም ተደራጊ ግስ። *ያለቀብ ላረጀ*።

ተግባር ስ ስራ፤ ድርጊት።

ተግባረ ስጋ ስ እንደ እርሻ፥ ንግድ የመሳሰለና በዚህ አለም ላይ ለመኖር የሚያስፈልግ ስጋዊ ስራ።

ተግባረ ነፍስ ስ እንደ ፆምና ፀሎት ያለና ለመንፈሳዊ ህይወት የሚያስፈልግ መንፈሳዊ ስራ።

ተግባረ እድ ስ እንደ አናጢነት፥ ሚካኒክነት፥…ያለ የእጅ ሙያ።

*ገበረ^2

ገበሬ ስ በእርሻ ስራ የሚተዳደር ሰው፤ አርሶ አደር፤ አርሶ በላ፤ አራሽ።

ገበሬ መጣኝ ቅ እንደ ገበሬው ጉብዝና ወይም ስንፍና በደንብ ወይም እየለገመ የሚያርስ በሬ፤ አቢያ በሬ።

ገበሬ ማህበር ስ ብዙ ገበሬዎች በህብረት ሰርተው ለመጠቀም የሚያቋቁሙት ማህበር።

ግብርና ስ የእርሻና የከብት እርባታ ስራ።

ገበር ስ እንደ ኮት፥ቀሚስ፥ ጃኬት፥… ባሉ ልብሶች ላይ በውስጥ በኩል የሚሰፋ፥ ብዙውን ጊዜ ለስላሳና ስስ የሆነ ጨርቅ።

ገበር ምጣድ ስ እንደ ምጣድ ጠፍጣፋ ሆኖ ሆሪያውን ጠርዙ እንደ ጎድጓዳ ሳህን ከፍ ያለና ከሸክላ የሚሰራ የዳቦ መጋገሪያ።

ገበርባሬ ስ ሰፋፊ በሆነ ጥቁር፥ ቀይና ቢጫ ጥለት ይሰራ የነበረ የሃር ልብስ።

ገበር እንጧይ ስ ነጣ ያለ ሰፋፊ ቅጠል ያለው ቅጠሉም ግንዱም እሾሃማ የሆነ ፍሬው ሲበስል ሎሚ የሚመስልና በአንዳንድ አካባቢዎች

እንደሳሙና ለልብስ ማጠቢያነት የሚያገለግል አነስተኛ የእፅዋት አይነት፤ ፍሬውም ገበር እንዲሁ ይባላል።

ገበርዲን ስ ለኮትና ለሱሪ የሚሆን የሱፍ ጨርቅ አይነት።

***ገበሰበሰ**

ግብስብስ ስ 1. ጥራጊ፣ ቆሻሻ። 2. ቅ (ዘይ.) ከጥራቱ ይልቅ ብዛቱ ያመዘነ።

ተግበሰበሰ ግ 1. የሚፈለገውም የማይፈለገውም በብዛት ተሰበሰበ፣ ተከማቸ። 2. ረጅም ልብስ ለብሶ ተንጋፈፈ፣ ተጎተተ፣ ተንዘረፈፈ።

አግበሰበሰ ግ 1. በብዛት ሰበሰበ፣ ወሰደ። 2. ያገኘውን ሁሉ ሳይመርጥ በላ። 3. ጥራቱን ሳይጠብቅ ያገኘውን ሁሉ ሰበሰበ፣ አከማቸ። 4. ጎተተ፣ አንዘረፈፈ (ልብሱን)።

ገበታ ስ 1. ከመቃ ወይም ከቀርከሃ ባለእግር ሆኖ የሚሰራና እንደ መሶብ ያለ እቃ። 2. ማእድ፣ ምግብ የቀረበበት እቃ። 3. ከእንጨት ተጠርቦ የሚሰራ በመፅሃፍ ጥራዝ ግራና ቀኝ ላይ የሚገኝ የመፅሃፍ አቃፊ። 4. ዋልታ። 5. ገበቴ። 6. አስራ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሚሆኑ ትናንሽ ክብ ጉድጓዶች ያሉት ከእንጨት የሚሰራ የገበጣ መጫወቻ።

ገበታ(ማእድ) ዘረጋ ምግብ አቀረበ።

ገበታ ጣለ ዝ.ክ.

ገበታው ደነገጠ የቀረበው ምግብ በሙሉ ተሟጥጦ ተበላ፣ ምንም ሳይተርፍ ቀረ።

ገበታ አስደንጋጭ (ስድብ) የሚቀርብለትን በሙሉ ምንም ሳያስቀር የሚበላ።

የገበታ መዝገበ ቃላት ስ በቀላሉ ከአንድ ቦታ ወደሌላ ቦታ ለማዘዋወር የማይቻል በመሆኑ አንድ ቦታ ተቀምጦ ለማመሳከሪያነት የሚያገለግልና ሰፋ ያሉ መረጃዎችን የያዘ ትልቅ መዝገበ ቃላት።

ገበታ ሃዋርያ ስ 1. "ግብረ ሃወርያ"ን ተመ.። 2. (ቤ.ክህ.) ልጆች ፊደል ተምረው ከጨረሱ በኋላ የሚማሩት የዮሃንስ መልእክት።

ገበታ ራስ ስ (ስድብ) ራሱ ትልቅና ጠፍጣፋ የሆነ (ሰው)።

ገበቴ ስ ከእንጨት የሚሰራ ሰፊና ጎድጓዳ የሆነ የቤት እቃ፤ ቆሬ።

***ገበዘ**

ግብዝ ቅ 1. ያልሆነውን እንደሆነ፣ የማይችለውን እንደሚችል ወይም ያላደረገውን እንዳደረገ አድርጎ የሚያስብና ያላግባብ ለራሱ ከፍተኛ ግምት የሚሰጥ (ሰው)። 2. ጥንካሬ የሌለው መናኛ ስራ።

ተገበዘ ግ ግብዝ ሆነ።

ገበዝ (ቄስ ገበዝ) ስ (ኢ . ኦ. ተ. ቤ.) በቤተክርስቲያን ቅፅረ ግቢ ውስጥ ያለውን የቤተ ክርስቲያን ንብረት የመጠበቅና የመንከባከብ ሃላፊነት የተሰጠው ካህን።

ግብዝና ስ የገበዝነት ስራ።

ገበየ ግ ገዛ፣ ሸመተ።

ገበያ ስ 1. የንግድ ልውውጥ የሚካሄድበት ቦታ። 2. (ዘይ.) ሰው የበዛበት፣ ጫጫታና ሁካታ የሞላበት ስፍራ። 3. ቶሎ የመሸጥ፣ የመግዛት ሁኔታ፣ ተፈላጊነት። *ገበያ የለው/ገበያው ሞቷል።*

ለገበያ ቀረበ ለሽያጭ ቀረበ።

[ከ] ገበያ ላይ ዋለ ዝ.ክ.

ገበያ ቆመ መሸጥና መለወጥ ተጀመረ (በገበያ ቦታ)።

ገበያ አወጣ በጥሩ ዋጋ ተሸጠ።

ገበያ ያውቃል ጥሩ እቃ መርጦ መግዛት ወይም በደህና ዋጋ መግዛትና መሸጥ ያውቃል።

ገበያው ተፈታ ገበያው ተበተነ ወይም አበቃ።

ገበያው አበደ በገበያ ላይ ለሽያጭ የቀረበው እቃ ተወደደ።

ገበያው ጠገበ ገበያው ላይ የሚሸጠውና የሚለወጠው ነገር ተትረፈረፈ።

ገበያተኛ ስ ገበያ ተገኝቶ የሚሸጥ ወይም የሚገዛ ሰው።

ግብይት ስ የመሸጥና የመግዛት ተግባር።

ተገበያየ ግ የመሸጥና የመግዛት ተግባር አከናወነ፣ ተሻሻጠ፣ ተገዛዛ።

ገበደ ግ ግንድን ወይም እንጨትን በወፍራሙ ፈለጠ።

ግብዳ ቅ 1. በወፍራሙ የተፈለጠ (እንጨት)። 2. (ዘይ.) በጣም ትልቅ፣ ግዙፍ።

***ገበደደ**

ተግበደደ ግ ሊያልቅ ተቃረበ፣ ጥቂት ቀረ።

አግበደደ ግ ሊጨርስ ተቃረበ፣ ጥቂት ቀረው።

***ገበገበ**

ግብጋባ ቅ (ስድብ) ንፉግ፣ ስስታም።

ግብግብ አለ ግ ተንገበገበ።

ተንገበገበ ግ 1. ተንሰፈሰፈ፣ ተስገበገበ። 2. ንፉግ፣ ስስታም ሆነ። 3. ከፍተኛ የሆነ ስሜት ተሰማው (የሃዘን፣ የቁጭት፣ የንዴት፣ የፍቅር፣ ...)። 4. በጣም ተቃጠለ፣ ተለበለበ (ለምሳሌ በህመም)።

አንገበገበ ግ 1. አንሰፈሰፈ፣ አስገበገበ። 2. ንፉግ፣ ስስታም አደረገ። 3. አበገነ፣ አቃጠለ (ነገር፣ ሃዘን፣ ፍቅር፣...)። 4. በጣም አቃጠለ፣

ሰበሰበ።

እንግብጋቢ ቅ አስቸኳይ፣ አጣዳፊ፤ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ።

ገበጣ ስ 1. ዝርግ ሆኖ የጠጠር ማስቀመጫ የሚሆኑ አስራ ሁለት ትናንሽና ክብ ጉድጓዶች ያሉት፣ ከእንጨት ወይም ከድንጋይ፣... የሚሰራ መጫወቻ፤ ገበታም ይባላል። 2. በገበጣ መጫወቻ ላይ ባሉ 12 ጉድጓዶች ውስጥ በሚጨመሩ 48 ጠጠሮች አማካኝነት የሚካሄድ ጨዋታ።



ገበጣ 1ኛ ፍቺ

ገቢር "*ገበረ^{1}" ስር ተመ.

ገባ ግ 1. ወደ ውስጥ ጠለቀ፣ ሰጠመ፣ ዘለቀ። 2. አንድ ላይ ሆነ፣ ተባበረ፤ አባል ወይም ተሳታፊ ሆነ፣ በአንድ ስራ ወይም ድርጊት ላይ ተሰማራ። *እድር ገባ /ትምህርት ቤት ገባ / ዘበኝነት ገባ።* 3. ተጨመረ፣ ተቀላቀለ። *ወጡ ውሃ ገብቶበታል።* 4. ጀመረ (ክረምት፣ ዘመን፣...)። 5. ተቀጠረ፣ ጀመረ። *ስራ ገባ።* 6. መጣ ወይም ሄደ፣ ደረሰ ። *አዲስ አበባ ትናንት ሌሊት ገባ።* 7. ተቀጠለ፣ መስመር ተዘረጋ። *መብራት ገባ።*

ገባው አወቀ፣ ተረዳ።

ያገባኛል (ጉዳዩ) ይመለከተኛል።

ግቢ ነፍስ ውጪ ነፍስ ስቃይ፣ ጣር፣ ጭንቅ።

ግባ በገመዱ እኔ በሰራሁት ጥፋት አንተ ተቀጣ፤ ተጠየቅ።

መግቢያ ስ 1. ወደ ውስጥ የሚታለፍበት በር። 2. መጠጊያ፣ መጠለያ፣ መሄጃ። *እህቴ ከሞተች ሌላ መግቢያ የለኝም።* 3. የሚደረገውን ነገር ለማየት ወይም በሚከናወነው ድርጊት ላይ ተሳታፊ ለመሆን የሚያስችል (ትኬት፣ ካርድ፣...)። 4. አንድ በስፋት ወይም በዝርዝር ሊቀርብ ለታሰበ ነገር (መፅሃፍ፣ ንግግር) እንደ ማስተዋወቂያ ወይም መንደርደሪያ ነጥብ ሆኖ የሚቀርብ ፅሁፍ፣ ንግግር፣...። 5. መጀመሪያ። *ክረምቱ መግቢያ ላይ ይመጣል።*

መግቢያ ዋጋ ስ ትያትር፣ ሲኒማ፣ ስፖርት፣... ለማየት የሚከፈል ገንዘብ።

ይግባኝ ስ (ህግ) በተሰጠ ውሳኔ (ፍርድ) ቅር የተሰኘ ወገን ጉዳዩ በበላይ አካል እንደገና እንዲታይ የሚያቀርበው አቤቱታ፣ ጥያቄ ።

ይግባኝ ሰሚ (ህግ) የይግባኝ ጥያቄን የማየት ስልጣን ያለው የበላይ አካል።

ገቢ ስ 1. ለኑሮ ወይም ለመተዳደሪያ የሚሆን ገንዘብ። 2. በእለት፣ በወር፣... ከሽያጭ ወይም ከሌላ የገቢ ምንጭ የሚገኝ ገንዘብ።

የገቢ ምንጭ ስ ለኑሮ ለመተዳደሪያ፣... የሚሆን ገንዘብ የሚገኝበት መንገድ፣ ዘዴ፣ ስራ።

ጋብቻ ስ 1. አንድ ወንድና አንዲት ሴት በትዳር (ባልና ሚስት ሆነው) ለመኖር እንዲችሉ የሚፈፅሙት ስነስርአት፣ ቃል ኪዳን። 2. ትዳር። አንድ ወንድና ሴት ህጋዊ በሆነ መንገድ አብረው ለመኖር የሚያስችላቸው የኑሮ ትስስር፤ ትዳር።

የጋብቻ ቀለበት ስ ባልና ሚስት በተጋቡ እለት ወይም እጮኞች በተጫጩ እለት አንዳቸው ላንዳቸው የሚያደርጉት የቃል ኪዳን ምልክት የሆነ ቀለበት።

ግቢ ስ 1. ጋብቻ። 2. መኖሪያ ቤት፣ መስሪያ ቤት፣... ያለበትና ዙሪያውን በአጥር የተከለለ ቦታ። 3. እንደ ቤተ መንግስት፣ ዩኒቨርሲቲ ያለ ቦታ።

ግባተ መሬት (ግብአተ መሬት) ስ 1. ሬሳ ወደ መቃብር ሲወርድ ወይም ሲገባ የሚደረገው ስነስርአት፣ ፀሎት። 2 (ዘይ.) የአንድ ነገር ማብቂያ ወይም ፍፃሜ ።

ግብ ስ 1. በእግር ኳስ፣ በእጅ ኳስ፣ በገና ጨዋታ፣... ላይ ኳሷ ወይም እሩሯ በአጥቂው ቡድን ተመትታ ወይም ተወርውራ የምታርፍበትና ነጥብ የምታስቆጥርበት ቦታ፤ ጎል። 2. በእግር ኳስ፣ በእጅ ኳስ፣ በገና ጨዋታ፣... ላይ ኳሷ ወይም እሩሯ በአጥቂው ቡድን ተመትታ ጎል ውስጥ መግባት። 3. አላማ።

ግቡን መታ የታቀደው ወይም የታለመው ተፈፀመ፣ ተሳካ ወይም ያቀደውን ወይም ያለመውን ፈፀመ፣ አሳካ።

ግብ አስቆጠረ ጎል ወይም ግብ አገባ።

ግበቡ(ግቡቡ) ቅ ተግባቢ፣ ተስማሚ። *ከሰው ሰው ጋር ግቡቡ ነው።*

በሚገባ በደንብ፣ በትክክል።

በተገባ ግ ተገቢ በሆነ። *ጉዳዩን ላስቀድመው ልትነግረኝ በተገባ ነበር።*

አይገባም አያስፈልግም፣ መሆን የለበትም።

የሚገባ አስፈላጊ፣ ትክክል።

የተገባ ዝ.ክ.

ተገቢ ቅ መሆን ያለበት፣ የሚገባ፣ ትክክል።

ተጋባ ግ 1. በአንድ እቃ ውስጥ የነበረው ነገር ወደ ሌላ ቦታ ወይም እቃ ተዛወረ፣ ተገለበጠ። 2. ባዶ ሆነ (ውስጡ የነበረው ነገር ወደ ሌላ እቃ ስለተዛወረ ወይም ስለተገለበጠ)። 3. ተላለፈ፣ ተዛመተ (ለምሳሌ በሽታ)። 4. ጋብቻ ፈፀመ። 5. በጋብቻ ዝምድና ተሳሰረ፣ ተዛመደ።

ተጋቦ ስ የበሽታ ከአንዱ ወደ ሌላው ሰው መተላለፍ።

ተግባባ ግ ተስማማ፤ ተወዳጀ፣ ተለማመደ።

ተግባቢ ቅ ከሰው ጋር ቶሎ የሚወዳጅ፣ የሚግባባ።

አገባ ግ 1. ውጭ የነበረውን ወደ ውስጥ አደረገ፣ ከተተ፣ ጨመረ። 2. ትዳር ያዘ፣ ጋብቻ ፈፀመ።

ኣያገባህም ጉዳዩ ኣይመለከትህም፥ ሊያሳስብህ ወይም ልትሳተፍበት ኣያስፈልግም።

ኢጋባ ግ 1. ጋብቻ እንዲፈፅም ኣደረገ። 2. ኣስተሳሰረ፥ ኣዛመተ (ለምሳሌ በሽታን)። 3. ኣንድን ነገር ከኣንድ እቃ ወደ ሌላ በመገልበጥ ወይም በማዛወር እቃውን ባዶ ኣደረገ ወይም ወደ ሌላ እቃ ገለበጠ፥ ኣዛወረ።

ኣግባባ ግ 1. ኣወዳጀ፥ እንዲቀራረብ ምክንያት ሆነ። 2. ኣባበለ፥ ገፋፋ። *ላብረው እንድሄድ ኣግባባኝ።*

ኣግባብ ስ 1. እውቂያ፥ ወዳጅነት። 2. ስነስርኣትን ወይም ደንብን የተከተለ ወይም ተገቢ የሆነ። *ኣግባብ ባለው መንገድ ኣልተሰራም።* 3. ግንኙነት። *ከጉዳዩ ጋር ኣግባብ ያለው መስሪያ ቤት።*

ገባሬ ሰናይ "*ገበረ¹" ስር ተመ.

ገባር "ገበረ¹" ስር ተመ.

ገብረ ጉንዳን ስ ጉንዳን።

ገብስ ስ ለእንጀራ፥ ለጠላ፥...የሚሆን የብርእ እህል።

ገብስ ነው ገራገር ነው፤ ክፋት የለውም፤ ቀላል ነው።

ገብስማ ቅ ኣልፎ ኣልፎ የነጭ ሰብጥር ያለበት ጥቁር ቀለም፥ የመልክ ኣይነት(ብዙውን ጊዜ ለጸጉር)።

ገብጋባ "ገበገበ" ስር ተመ.

የገቦ ነገር ኣድራጊው ወይም ኣስደራጊው የማይታወቅ።

የገቦ [እህል] ስ ሰብል በሚሰበሰብበት ጊዜ ማሳው ላይ ረግፎ የሚቀረውና እንደገና እዚያው ማሳ ላይ በቅሎ የሚገኝ እህል።

＊ገተለተለ

ግትልትል ስ የተያያዘ፥ ቅጥልጥል፥ ቁጥርጥር፥ ዝብዝንኪ ነገር።

ግትልትሳም ቅ (ስድብ) ኮተታም፤ ዝግንትሳም።

ግትልትል ኣለ ግ ተግተለተለ።

ግትልትል ኣደረገ ግ ኣግተለተለ።

ተግተለተለ ግ በብዛት ሆኖ ኣንዱ ኣንዱን እየተከተለ ተጓዘ፥ ተንጋጋ።

ኣግተለተለ ግ በብዛት በበቦ ኣመጣ ወይም ወሰደ፤ ኣንጋጋ።

ገተመ ግ እያፈሰ ቃመ (ቆሎን፥ ንፍሮን፥...) ።

ገተረ ግ 1. ወጠረ፥ ለጠጠ። 2. (ነውር) ኣቆመ፥ ቀሰረ (የወንድን ብልት)። 3. ያዘ፥ ኣስጠነቀ (በነገር፥...)። 4. ለረጅም ጊዜ ኣቁሞ ኣቆየ። *እመጣለሁ ብሎ ገትሮኝ ቀረ።* 5. ተቋቋመ፥ ኣልሸነፍ ኣለ። 6. ወደ መሬት ያለው ቀጥታንት የበዛ ሆነ፥ ጋደም ሳይል ቀረ (ከዋፈር ጋር ለተዋደደ ማረሻ፥ ለዶማ፥...)።

መገተሪያ ስ በውስጡ ቀጫጭን ሽቦዎች የተሰኩበት ወይም በሌላ ዘዴ ደርቆ እንዲል ተደርጎ የተሰራና የሙሽራ ልብስ ወይም ሌላ የሴት ቀሚስ ቡፍ ብሎ እንዲታይ የሚያደርግ ነገር፤ ቡፋንቲ።

ገታራ ቅ ግትር።

ግትር ቅ 1. ያልሰላ፤ በትክክል ያልተገጠመ፥ ወደ ውስጥ የሚወጋ (ማረሻ፥ እርፍ፥...)። 2. ሃሳቡን በቀላሉ የማይለውጥ ወይም የሌላውን ሃሳብ በቀላሉ የማይቀበል (ሰው)።

ተገተረ ግ 1. ቀጥ ብሎ ቆመ። 2. ሳያልቅ ቀረ (የቤት፥ የእጥር፥...ስራ)።

ተገትሮ ቀረች ሳታገባ ጊዜዋ ኣለፈባት።

ተጋተረ ግ ተያያዘ፥ ተጋፈጠ። *ስራውን ተጋትሮታል።*

ተግተረተረ ግ 1. ተውተረተረ፥ ተንገዳገደ። 2. ቆመ፥ ተገተረ (የደም ስር)።

ኣግተረተረ ግ 1. ኣውተረተረ፥ኣንገዳገደ። 2. ኣቆመ፥ ገተረ(የደም ስርን)።

ገተተ ግ 1. ተቦጫጨቀ፥ ተበጣጠሰ (በእርጅና ምክንያት)። 2. ነተተ።

ገታታ ቅ 1. (ስድብ) ከርፋፋ፥ ቂል፥ሞኝ። 2.ነታታ።

ግትት ስ 1. ያረጀ ወይም ያለቀ የስፌት እቃ፤ ግትቻ። 2. (ስድብ) ነታታ፥ ከርፋፋ፥ ሞኝ።

ግትት ዝ.ክ.

ግትቻ ስ 1. ያረጀ ወይም ያለቀ የስፌት እቃ። 2. (ስድብ) ሀ. የሸመገለ፥ ያረጀ (ሰው)። ለ.ቀርፋፋ፥ ገልጃጃ።

ተንጋተተ ግ ተንከረፈፈ።

ኣንጋተተ ግ ኣንከረፈፈ።

ገተገተ ግ 1. ቀረጠመ፥ኣኘከ (ህመም ሰውነትን)። 2. መጠመጠ፥ መገመገ፥ ጠባ (ጡትን)።

＊ገተገተ

ግትጋታ(ገተገት) ቅ 1.የያዘውን (ነገር፥ሃሳብ፥እምነት፥...)የማይለቅ፥ነዝናዛ፥መንቻካ። 2.ቀብቃባ።

ተንገታገተ ግ 1.የያዘውን (ነገር ሃሳብ፥ እምነት፥...) ላለመልቀቅ ባለው ኣቅም ተፍጨረጨረ፥ ተጣጣረ። 2.ተንቀበቀበ።

ገታ ግ 1. ኣቆመ፥ ኣገደ፥ ከለከለ፥ እንዳይቀጥል ኣደረገ። 2. ተወ፥ ኣቋረጠ።

ግት ስ የተገታ፥ የታደገ፥ እገድ።

ተገታ ግ 1. ታገደ፥ ተከለከለ፥ እንዳይቀጥል

ተደረገ፣ ቆመ። 2. ተቆጠበ፣ ተወ።

ገታራ "ገተረ" ስር ተመ.

ገታታ "ገተተ" ስር ተመ.

ገትጋታ "*ገተገተ" ስር ተመ.

***ገቸገቸ**

ገችጋቻ ቅ የማይሰግር ወይም መጋዣ የሆነ (በቅሎ፣ ፈረስ)።

ተንገቸገቸ ግ ዘከዘከ ወይም ዘጥ ዘጥ አለ።

አንገቸገቸ ግ አንገጫገጨ፣ ነቀነቀ።

ገች ስ 1. ጠላ የሚሞላበት ወይም የሚሸምበት ትልቅ ጋን። 2. ትልቅ ድልብ በግ፣ ፍሪዳ።

***ገነበጠ**

ግንብጥ ስ ገና ያልጠና ወይም ያልዘረዘረና ብቅ ብሎ የሚታየው የበቆሎ ወይም የብርእ እህል ፍሬ።

አገነበጠ ግ 1. በገኑ ላይ ፍሬ ሻጠ፣ አዘለ(የበቆሎ አገዳ)። 2. አገነደረ፣ ወገቡ ላይ ታጠቀ (ለምሳሌ ጎራዴን)።

ገነባ ግ 1. አነፀ፣ ግንብ ሰራ። 2. አዳበረ፣ አበለፀገ።

ገንቢ ቅ ጠቃሚ፣ ለእድገት የሚረዳ (አስተያየት፣ ሃሳብ፣...)።

ገንቢ ምግብ ቅ ሰውነትን ለመገንባት ወይም ለማደርጀት የሚያገለግል ፕሮቲንነት ያለው የምግብ አይነት።

ግንብ(ግምብ) ስ በድንጋይ፣ በኮሬት፣ በአሸዋና በሲሚንቶ፣... የታነፀ ወይም የተሰራ (ቤት፣ አጥር፣ ሀንፃ፣...)።

ግንበኛ(ግምበኛ) ስ የግንብ ስራ ባለሙያ።

ግንባታ (ግምባታ) ስ 1. የልማት፣ የእድገት እንቅስቃሴ። *የኢኮኖሚ ግንባታ*። 2. የማነፅ፣ የመገንባት ስራ።

ተገነባ ታነፀ፣ ተሰራ።

ገነተረ ግ 1. በደንብ ሳይሆን ላይ ላዩን በሰለ (ስጋ)። 2. አልታኘክ አለ፣ እኛ ሆነ (ስጋ)። 3. (ዘይ.) ሃሳቡን አልቀይር አለ፣ እምቢ አለ።

ግንታራ ቅ 1. በሚገባ ያልበሰለ ወይም የገነተረ (ስጋ) ስ 2. (ዘይ.) ሃሳበ ግትር።

ግንትር ቅ በሚገባ ያልበሰለ (ስጋ)።

አገነተረ ግ 1. በደንብ ሳያበስል ቀቀለ፣ አገነፈለ (ስጋን)። 2. ነገር እንዲባባስ ወይም እንዲጠነክር አደረገ።

ገነት ስ 1. በኦሪት ዘፍጥረት ምእራፍ 3. ላይ እንደተገለፀው አዳምና ሄዋን የፈጣሪያቸውን ትእዛዝ ተላልፈው ከመባረራቸው በፊት ይኖሩበት ነበር ተብሎ የሚታመንበትና በተለያዩ ተክሎች የተዋበ አስደሳች ቦታ። 2. እንደ ክርስትና ባሉ ሃይማኖቶች እምነት መሰረት ፃድቃን ወደ መንግስተ ሰማያት ከመግባታቸው በፊት ወይም እስከ እለተ ምፅአት የሚቆዩበት ሰማያዊ ቦታ። 3 (ዘይ.) በሁሉም ረገድ በጣም አስደሳች የሆነ ስፍራ፣ አካባቢ፣ ሃገር ።

የገነት ወፍ ስ 1. ጅራቷ ረጅም፣ መጠኗ ትንሽና መልኳ ሽልምልም የሆነ፣ በወንዝ አካባቢ የምትገኝ በመስከረምና በጥቅምት ወራት ብቻ የምትታይ ወፍ። 2. **"ጣዎስ"** ን ተመ.

ገነታ ግ በቁጣ ወይም በንዴት አነጋገር ጊዜ ድምፅ የተለመደ ቃናውን ለወጠ፣ ከረረ።

ገነነ ግ 1. ከፍ ከፍ አለ፣ በጣም ታወቀ፣ ዝነኛ ወይም ታዋቂ ሆነ። 2. አየለ፣ በረታ (ህመም፣ ነገር፣...)። 3. ጎልቶ ታወቀ ወይም ተሰማ(ጣእም)። 4. ለመለመ፣ አደገ (ተክል)።

ገናና ቅ ዝነኛ፣ ታዋቂ፣ ስመጥር።

ግነት ስ በልዩ ልዩ የፈጠራ ስራዎች (በስነፅሁፍ፣ በኪነጥበብ፣...) ውስጥ ደራሲው ሊያስተላልፍ የፈለገውን ሃሳብ ተደራሲው በደንብ እንዲረዳው ወይም እንዲሰማው ለማድረግ ሲባል አንድን ድርጊት ወይም ሃሳብ አጋኖ የማቅረብ ቴክኒክ ወይም ዘዴ ።

ተጋነነ ግ አንድ ነገር ከሚገባው ወይም ከሆነው በላይ (የተሻለ ወይም መጥፎ፣ ትልቅ ወይም ትንሽ፣...) እንደሆነ ተደርጎ ቀረበ።

አገነነ ግ 1. በጣም ትልቅ፣ ዋና፣... አድርጎ አቀረበ(ሰውን)። 2. ጎልቶ እንዲታወቅ ወይም እንዲሰማ አደረገ(ጣእምን)።

አጋነነ ግ አንድን ነገር ከሚገባው ወይም ከሆነው በላይ የተሻለ ወይም መጥፎ፣ ትልቅ ወይም ትንሽ፣... እንደሆነ አድርጎ አቀረበ።

***ገነኘ**

ግንኙነት ስ 1. ተመሳሳይነት። 2.ዝምድና፣ ቀረቤታ። 3. የተለያዩ ወገኖች ለተለያዩ አላማዎች (አብሮ ለመስራት፣ በአንድ የተወሰነ ጉዳይ ላይ ሃሳብ ለመለዋወጥ፣ ንግድ ለማካሄድ፣...) ሲሉ በመካከላቸው የሚፈጥሩት ቀረቤታ። 4. ወሲብ ወይም የግብረ ስጋ ድርጊት።

ግኝት ስ ስለአንድ ነገር ተፈጥሮ፣ ምንነት፣ አሰራር፣ ጥቅም፣... ምርምር ወይም ጥናት በማድረግ የታወቀ አዲስ መረጃ ወይም የተደረሰበት አዲስ ውጤት።

ተገኘ ግ 1. ጠፍቶ፣ ተደብቆ፣ ተረስቶ፣...የነበረው ወይም የሚፈለገው ነገር ወጣ፣ ተከሰተ፣ ተያዘ፣ በእጅ ተደረገ። 2. በአንድ የተወሰነ ቦታ፣ ድርጊት፣... ላይ ተሳታፊ ሆነ። *በስብሰባው ላይ ብዙ ሰው ተገኘ።*

የማይገኝ በጣም ጥሩ፣ ጥራት ያለው፣ ምርጥ፣ እንደልብ የሌለ። *የማህሌት ሴት የማይገኝ ነው።*

የተገኘውን ማንኛውንም፤ የሆነውን። *የተገኘውን ልብስ ለበሰ።*

ተገናኘ ግ 1. አብሮ ለመስራት ወይም በአንድ የተወሰነ ጉዳይ ላይ ሃሳብ ለመለዋወጥ፥... ሲል ከሌላ ወገን ጋር አንድ ቦታ ላይ ተሰባሰበ። 2. በአካል ተቀራረበ ተያየ፥ ተነጋገረ ወይም ተገጣጠመ። *ከስራ አለቃዬ ጋር ተገናኘ።* 3. ተያያዘ። 4. ወሲብ ወይም ሩካቤ ስጋ ፈፀመ።

መገናኛ ስ 1. በተለያዩ ወይም በተራራቁ ቦታዎች ላይ የሚገኙ ክፍሎችን ለማገናኘት የሚረዳ እንደ አይሮፕላን፥ መኪና፥ ሬድዮ፥ ስልክ፥ ፋክስ፥... ያለ መሳሪያ። 2. አንዱን ቦታ ከሌላው የሚያገናኝ መንገድ፥ መስመር። 3. ከተለያየ አቅጣጫ የሚመጡ መንገዶች የሚገጣጠሙበት ቦታ ወይም ስፍራ። ቅ 4. ግንኙነት ለማድረጊያ ወይም ለመሰባሰቢያ የሚሆን (ቦታ፥ ጊዜ፥ ምክንያት፥...)።

መገናኛ ብዙሃን ስ የተለያዩ መረጃዎችን፥ ዜናዎችን፥...በአንድ ጊዜ ለብዙ ሰው ለማሰራጨት የሚያገለግሉ እንደ ጋዜጣ፥ ሬድዮ፥ ቴሌቪዥን ያሉ የማሰራጫ አውታሮች፥ መሳሪያዎች።

አገኘ ግ 1. ጠፍቶ፥ ተደብቆ፤ ተረስቶ፥... የነበረን ነገር በእጁ አደረገ፥ ያዘ አስገባ፤ ጨበጠ። 2. የ__ባለቤት ሆነ። *ሃብት አገኘ።* 3. አንድ የተወሰነ ቦታ ላይ ተገጣጠመ፥ ተያየ፥...። *ትላንት ሲኒማ ቤት አገኘሁት።* 4. አወቀ፥ ደረሰበት። *የጠፋውን መንገድ አገኘው።* 5. አጋጠመ። *ችግር አገኘው።*

አገናኘ ግ 1. ግንኙነት እንዲኖራቸው አደረገ(ለስራ፥ አንድ የተወሰነ ጉዳይ ላይ ለመነጋገር ወይም ለሌላ አላማ)። 2. ተለያይቶ ወይም ተራርቆ የነበረው እንዲቀራረብ አደረገ። 3. ተለያይቶ የነበረውን አያያዘ፥ አጣበቀ (ለምሳሌ የኤሌክትሪክ ሽቦን)።

አስገኘ ግ 1. በፊት የሌለ ወይም ያልነበረ ነገር እንዲኖር አደረገ። 2 እንዲገኝ አደረገ።

ገነዘ ግ ከፈነ።

መግነዣ ስ ከፈን።

ግንዘት ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ .) ለሞተ ሰው ፍትሃት ወይም ፀሎት የሚደረግበት የፀሎት መፅሃፍ።

ግንዝ ቅ የተገነዘ (ሬሳ)።

***ገነዘበ**

ግንዛቤ ስ 1. ልብ ማድረግ፤ መረዳት። 2. እውቀት። *ከልምምድና ጥሩ ግንዛቤ ይገኛል።*

ተገነዘበ ግ ልብ አደረገ፥ አስተዋለ፤ ተረዳ፤ አወቀ።

ተገናዘበ ግ ተነፃፀረ፥ ተመሳከረ።

አገናዘበ ግ 1.አስተዋለ።2.አነፃፀረ፥ አመሳከረ።

አገናዛቢ አፀፋ ስ (ሰዋ.) ባለቤትነትን የሚያመለክት ተውላጠስም (ምሳሌ፥ ቤት ___ ቤትህ /አባት አባቷ።

አስገነዘበ ግ 1. አሳወቀ፥ አስረዳ። 2. አስታወቀ፤ አሳሰበ።

ማስገንዘቢያ ስ 1.ማሳሰቢያ።2.ማስገንዘቢያ።

***ገነደረ**

አገነደረ ግ ታጠቀ፤ አገነበጠ (ለምሳሌ ጎራዴን)።

አጋንዱር ቅ 1. ወደል፥ ጠብደል። 2. ዘርጣጣ፤ እንቅብ ሆድ።

ገነደሰ ግ 1. ቆርጦ ጣለ፤ ገረሰሰ (ዛፍን)። 2. አጋደመ፤ ደበለለ፤ አስተኛ።

ገንዳሳ(ግንድስ) ቅ (ስድብ) መተኛት የሚያበዛ፤ እንቅልፋም።

ገንደስ ገንደስ አለ ግ ፊንደስ ፊንደስ እያለ ቀስ ብሎ ተራመደ (ወፍራም ሰው)።

ተገነደሰ ግ 1.ተቆርጦ ወደቀ፤ ተገረሰሰ (ዛፍ)። 2. ተንደባለለ፤ ወደቀ። 3. ተጋደመ፤ ተኛ።

ገነገነ ግ ጠረጠረ፤ ሰጋ።

ገንጋና ቅ ጠርጣሪ።

ገንጋኝ ዝ.ከ.

ግንገና ስ ጥርጣሬ፥ ፍርሃት፤ ስጋት።

አገነገነ ግ ገነገነ።

ገነጠለ ግ 1. ዘነጠለ፤ ዘነጠፈ፤ ለየ (ለምሳሌ የዛፍ ቅርንጫፍን)። 2. ተያይዘው ወይም ተጣብቀው የነበሩትን ለያየ፤ ነጠለ፤ ቀደደ (፡ ገፁን የመፅሃፍ ሽፋንን፡...ከጥራዙ ላይ)። 3 አንድ የነበረውን ለያየ፤ ከፋፈለ (ለምሳሌ ሃገርን)።

ግንጣይ ቅ 1. ተገንጣይ። 2. የሃገርን የተወሰነ ክፍል ለመገንጠል ወይም ለመለየት የሚታገል ወይም ይህ አላማ ያለው (ድርጅት፡ቡድን፥...)።

ግንጣይ ቅ ከዋናው ዛፍ ወይም ከግንዱ የተቆረጠ፤የተለየ፤...ቅርንጫፍ።

ግንጥል ቅ ከመሰሉ፤ ከወገኑ የተለየ ወይም የተገነጠለ።

ግንጥል ጌጥ ስ አብሮት ካለው ጋር የማይስማማ ወይም ያልተሟላ ጌጥ።

ተገነጠለ ግ 1. ተዘነጠለ፥ ተዘነጠፈ፤ ተለያየ (ለምሳሌ የዛፍ ቅርንጫፍ)። 2. ተለያየ፥ ተላቀቀ፤ ተቀደደ (ገፅ፥ የመፅሃፍ ሽፋን፥...)። 3.ተለየ ብቻውን ሆነ ወይም ብቻውን መተዳደር ጀመረ። 4. ተለያየ (መንገድ)።

ተገንጣይ ቅ ከአንድ አገር ውስጥ የተወሰነውን ክፍል ወይም አካባቢ ነጥሎ ወይም ለይቶ ለብቻ የማድረግና ሌላ መንግስት የመመስረት አላማ ያለው ድርጅት ወይም ቡድን።

ገነፈለ ግ 1. ፈልቶ ፈሰሰ። 2. ታምቆ፥ ታግዶ የነበረው ፈንቅሎ ወጣ (እንባ፥እምባ፥...)። 3.(ዘይ.)ተቆጣ፥ ቱግ አለ።

ተገነፈለ ግ በደንብ ሳይበስል በውሃ ብቻ ተቀቀለ (ለምሳሌ ስጋ፥ የራስ ባቄላ)።

አገነፈለ ግ በደንብ ሳያበስል በውሃ ብቻ ቀቀለ።

*ገነፋ

ገንፎ ስ የገብስ ወይም የስንዴ፥... ዱቄት የፈላ ውሃ ውስጥ ተጨምሮ በማማሰያ በመፍረሙ እየታሸ ከበሰለ በኋላ በቅቤ፥ በዘይት፥ በብጥብጥ ተልባ፥... የሚበላ ምግብ።

ተገነፋ ግ 1. ገንፎ ተሰራ። 2. እንደ ገንፎ ሆኖ ተሰራ።

አገነፋ ግ 1.ገንፎ አዘጋጀ። 2. እንደ ገንፎ አድርጎ ሰራ። 3. በማማሰያ አሸ፥ ሳገ (ገንፎን)።

ገና ተው.ግ ያልተፈፀመን፥ ያልተደረገን፥ ያልደረሰን፥ያልተሟላን፥...ወይም ወደፊት የሚፈፀምን፤ የሚደረግን፤ የሚሆንን ነገር፥ ጉዳይ፥...ለማሳየት ወይም ለመግለፅ የሚያገለግል ቃል። *ምሳሌ፦ ገና አልበላሁም /ሁለተኛ ደረጃን ገና አልጨረሰም።*

ገና ለገና ምን አልባት፤ ወደፊት።

ገና ስ 1. በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ ታህሳስ 29 ወይም በየአራት አመቱ በዘመነ ዮሃንስ ብቻ ታህሳስ 28 ቀን የሚከበር፥ ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደበት ቀን፤ ልደት። 2. የገና ጨዋታ።

ገና መምቻ ስ 1. ሩር ወይም ጥንግ የሚመታበት፥ በአንድ በኩል ከጫፉ ቀልበስ ያለ ብትር። 2. የገና መጫወቻ ሜዳ ክልል።

ገና ተሳዳቢ ስ የገና እለት የገና ጨዋታ ተሸናፊውን ወገን በሆታና በግጥም የሚሳደብ የአሸናፊው ወገን አቀንቃኝ።

የገና ጀንበር ስ ቀኑ አጭር ሌሊቱ ደግሞ ረዥም የሚሆንበት ወቅት።

የገና ጨዋታ የገና እለት ወንዶች በሁለት ቡድን ተከፋፍለው ሩርን ወይም ጥንግን በገና መምቻ እየመቱና ግብ እያገቡ አሸናፊ ለመሆን የሚወዳደሩበት ጨዋታ።

ገናና "ገነነ" ስር ተመ.

ገንቢ "ገነባ" ስር ተመ.

ገንባሌ "ገምባሌ" ን ተመ.

ገንቦ (ገምቦ) ስ ከእንስራ አነስ፥ ከምንቸት ከፍ የሚልና ከሸክላ የሚሰራ የጠላ፥ የጠጅ፥የውሃ፥... መያዣና ማቅረቢያ እቃ (ሸክላ ስር ተመ)።

ገንቦሬ "ጎምበሬ" ን ተመ.

ገንታራ "ገነተረ" ስር ተመ.

ገንዘብ ስ 1. በመግዛትና በመሸጥ ሂደት ውስጥ ሻጭና በገዥ መካከል ተቀባይነት ያለው ለመገበያያ የሚያገለግል ነገር፥ አብዛኛውን ጊዜ ከመዳብ ፥ ከብር ወይም ከወርቅ፥... የሚሰራና የተወሰነ ልክ ላዩ ላይ የታተመበት የሳንቲም ወይም የወረቀት መገበያያ። 2. ንብረት።

ገንዘቤ ነው የግሌ፥ ንብረቴ ነው።

ገንዘብ ቋጠረ ገንዘብ አጠራቀመ።

የገንዘብ ቅጣት ስ የተወሰነ ገንዘብ በማስከፈል የሚፈፀም የቅጣት አይነት።

ገንዘብ ቤት ስ 1. በአንድ መስሪያ ቤት ወይም ድርጅት ውስጥ ገንዘብ የሚቀመጥበት ክፍል። 2. ገንዘብ ያዥ።

ገንዘብ ከፋይ ስ በአንድ መስሪያ ቤት ወይም ድርጅት ውስጥ ደመወዝ ወይም ሌላ ወጭን የመክፈል ስራ የሚሰራ ሰው።

ገንዘብ ያዥ ስ በአንድ መስሪያ ቤት፥ ድርጅት ወይም እንደ እድር፥ ማህበር ባሉ ማህበራዊ አካላት ውስጥ ተቀማጭ ወይም ተንቀሳቃሽ የሆነውን ገንዘብ በሃላፊነት ተረክቦ የሚይዝ ሰው።

ገንዳ ስ 1. ወፍራም ግንድን አጎድጎ በመቦርቦር የሚዘጋጅና ለከብቶች ውሃ መጠጫነት የሚያገለግል እቃ። 2. ሰው ውስጡ ገብቶ ሊታጠብበት የሚችል በባኞ ቤት ውስጥ የሚገኝና ከሸክላ ወይም ሴራሚክስ፥... የሚሰራ እቃ።

ገንዳሳ "ገነደሰ" ስር ተመ.

ገንገበት ቅ 1. (ስድብ) ያልሰለጠነ፥ ከርፋፋ። 2. ገብጋባ፥ስስታም።

ገንጋና "ገነገነ" ስር ተመ.

ገንጋኝ ዝ.ከ.

ገንጣይ "ገነጠለ" ስር ተመ.

ገንፎ "*ገነፋ" ስር ተመ.

*ገወለለ

ተንገዋለለ (ተንጓለለ) ግ 1. ቆሻሻው ከደህናው ወይም ደህናው ከቆሻሻው በሰፌድ ወይም በወንፊት፥... አማካይነት ተለየ (ለምሳሌ ቆሻሻ ያለበት እህል)። 2. (ዘይ.) ስራ ፈቶ ዞረ፥ ተንገላወደ።

አንገዋለለ ግ 1. ቆሻሻውን ከደህናው ወይም ደህናውን ከቆሻሻው ለመለየት በሰፌድ ወይም በወንፊት ላይ አድርጎ ሰፌዱን ወይም ወንፊቱን ወደፊትና ወደኋላ አንቀሳቀሰ ወይም አዞረ (ብዙውን ጊዜ ለእህል)። 2. አገለለ፥ ለየ። 3(ዘይ.)አዞረ፥ አንከራተተ።

እንግውላይ ስ ከተፈለገው እህል ወይም ጥራጥሬ ላይ ተለይቶ የሚቀረውና የማይፈለገው የእህሉ ወይም የጥራጥሬው ክፍል ወይም ቆሻሻ፥

ብጣሪ።

ገውዝ [ንፍስ] ስ በግንቦት የሚወጣ የኮከብ ስም። በተጨማሪ "**ኮከብ ቆጠራ**"ን ተመ.

ገውጋዋ ቅ 1. ሞኝ፣ ቂል። 2. ዘዋሪ፣ ቀውላላ።

ገዘረ "ገረዘ"ን ተመ

ገዘተ ግ አንድ የተወሰነ ድርጊት እንዳይደረግ ከለከለ፣ አወገዘ(የክህነት ስልጣን ያለው ሰው)።

ግዝት ስ እንዳይደረግ ካህን የከለከለው ነገር።

ተገዘተ ግ 1. አንድን የተወሰነ ድርጊት እንዳያደርግ ተከለከለ፣ ተወገዘ (በካህን)። 2. ማለ።

ገዘገዘ ግ 1. ለመቁረጥ ከረከረ። 2. ቀስ በቀስ አዳከመ፣ አቅም አሳጣ፣ ውስጥ ውስጡን ቦረቦረ። *የነበረውን መንግስት ተቃዋሚዎቹ ገዝግዘው ጣሉት /በሽታ ገዝግዞ ገደለው።*

ተገዘገዘ ግ 1. ተከረከረ። 2. ተዳከመ፣ አቅም አጣ፣ ተቦረቦረ።

***ገዘገዘ**

ገዝጋዛ (ገዘገዘ) ቅ 1. ነገር የማይቆርጥ፣ ወቅሚቃ፣ ነዝናዛ። 2. ሲናገር ወይም ሲያነብ ድምፁ የሚንቀጠቀጥ። 3. አንድን ስራ በቅልጥፍና የማይሰራ፣ ቀርፋፋ።

ተንገዘገዘ ግ 1. ተንገዳገደ። 2.ፊደሎችን እየቆጠረና እየጎተተ አነበበ ወይም ተናገረ።

አንገዘገዘ ግ አንገዳገደ።

ገዘፈ ግ 1. በጣም ወፈረ፣ ደነደነ። 2. ረቂቅ የነበረው በአካል ወይም በቅርፅ ጎልቶ ታየ፣ ተከሰተ። 3. አጓራ (በዛር ምክንያት)።

ግዙፍ ቅ በጣም ወፍራም ወይም ትልቅ።

ግዝፈት ስ ውፍረት።

አገዘፈ ግ ትልቅ፣ ጉልህ ሆኖ እንዲታይ አደረገ።

ገዛ ግ 1. ገበየ፣ ሸመተ። 2. አስተዳደረ፣ መራ (መሪ፣ ባለስልጣን)። 3. አፈራ፣ አበጀ። *በገንዘቡ ወዳጅ ገዛ።*

በገዛ እጁ በሌላ ሳይሆን እራሱ በራሱ። *በገዛ እጁ ተሰቀለ።*

የገዛ ራሱ የራሱ፣ የግሉ።

መግዣ ስ መገብያ ገንዘብ።

ገዥ ስ የበላይ አስተዳዳሪ፣ ባለስልጣን(ለምሳሌ አገረ ገዥ፣ የባንክ ገዥ)።

ግዛት ስ 1. የተወሰነ የአስተዳደር ክልል። 2. ክልል።

ግዥ ስ የመግዛት ተግባር።

ተገዛ ግ 1. ተገበየ፣ ተሸመተ። 2. ተመራ፣ ተዳደረ።

አገዛዝ ስ አስተዳደር።

ገዝጋዛ "*ገዘገዘ" ስር ተመ.

ገዠሞ "ገጀሞ" ን ተመ.

ገዥ "ገዛ" ስር ተመ.

***ገየጠ**

ጌጥ ስ አንድን ነገር ለማስዋብ የሚያገለግል እንደ ወርቅ፣ ብር፣ አልማዝ፣ ጥልፍ፣... ያለ ነገር።

ጌጠኛ ቅ በጌጥ የተዋበ።

ጌጣጌጥ ስ ልዩ ልዩ አይነት ጌጥ።

ተጌጠ ግ በጌጥ ተዋበ፣ አማረ።

ተጊያጊያጠ ግ ተሸቀረቀረ፣ የተለያዩና የሚያሳምሩ ነገሮችን በመጠቀም ተዋበ።

አጌጠ ግ ተሽላለመ፣ አማረ፣ ተዋበ።

አስጌጠ ግ በጌጥ እንዲያምር ወይም እንዲዋብ አደረገ።

ገደቢስ "ገድ" ስር ተመ.

ገደለ ግ 1. ህይወት አጠፋ፣ እንዲሞት አደረገ። 2. እንዳይኖር አደረገ፣ አጠፋ (ስሜትን፣ ሞራልን፣...)። 3. እንዳይከናወን አደረገ። *ስራውን ገደለው።* 4. ጎዳ፣ አደከመ። *ፀሃዩ ገደለው።*

ገዳይ ቅ የሰው ህይወት ያጠፋ(ሰው)። 2. አዳኝ። *ገዳዩ ዝሆን ገድሎ ተመለሰ።*

ግዳይ ስ በጦርነት የተሳተፈ ሰው ጠላት ለመግደሉና የጀግንነት ስራ ለመፈፀሙ የሚጠቅሰው ማስረጃ፣ የሚያቀርበው ምርኮ ወይም አዳኝ አድኖ የሚያቀርበው አውሬ፣ እንስሳ ወይም ከታደነው እንስሳ ወይም አውሬ አካል ላይ ተወስዶ ለማስረጃነት የሚቀርብ ምልክት።

ግዳይ ጣለ በጦርነት የተሳተፈ ሰው ስለፈፀመው ጀብድ ምስክር በመጥቀስ በሽለላና በፉከራ ተናገረ ወይም ምርኮውን አቀረበ ወይም አዳኝ ያደነውን አቅርቦ አሳየ።

ግድያ ስ 1. የመግደል ተግባር። 2. ሽሚያ፣ ርብርቦሽ፣ ትግል። *ሊቀውን ያገኘሁት በስንት ግድያ ነው።*

ተገደለ ግ እንዲሞት ተደረገ።

ተጋደለ ግ አንድ ነገር ለማግኘት ወይም ለመፈፀም ከፍተኛ ጥረት አደረገ፣ በጣም ታገለ፣ ተሟሟተ።

ተጋዳይ ቅ ለአገር ነፃነትና ለክብር ወይም ለቆመለት አላማ ሲል ህይወቱን አሳልፎ የሚሰጥ።

ተጋድሎ ስ አንድን አላማ ለማሳካት የሚደረግ ከፍተኛ ትግል።

አጋደለ ግ አሸማ፡ አራከተ፡ አታገለ።

ገደል ስ 1. ውሃ ወይም ሌላ ነገር የበረበረውና ወደታችና ወደጎን ርዝመት ያለው ቦታ፡ አዘቅት። 2. ከተራራ ጫፍ እስከ ግርጌ ያለ የመሬት አካል።

ገደል ገባ 1. ተበላሸ፡ ያለውጤት ቀረ። 2. ትልቅ ችግር ላይ ወይም ስህተት ላይ ወደቀ። 3. ከገደል ጫፍ ላይ ወደ ታች ወደቀ።

ገደላገደል ገደል የበዛበት።

የገደል ማሚቶ ስ 1. በገደል ወይም እንደ ገደል ባለ ነገር አካባቢ ሲጮሁ ከገደሉ ጋር ተጋጭቶ የሚመለስና በተመሳሳይ መልክ የሚሰማ ጩኸት፤ ድምፅ። ቅ 2. (ዘይ.) የራሱን ሳይሆን የሌላ ሰው ሃሳብ የሚያስተጋባ (ሰው)።

ገደላማ ቅ ገደላገደል።

ገደመ ግ ገዳም እንዲሆን አደረገ።

ገዳም ስ መነኩሳት ከዓለማዊ ኑሮ ተገልለው በሃይማኖታዊ ስርአትና ደንብ እየተዳደሩ የሚኖሩበት ቤተክርስቲያን ያለበት ቦታ።

ገዳም ገባ ዓለማዊ ኑሮን በመተው መንፈሳዊ ኑሮን ለመኖር ገዳም ውስጥ መቀመጥ ጀመረ፡ መነነ።

የገዳም አባት ስ የገዳም ሹም፡ የመነኩሳት አስተዳዳሪ፤ አበምኔት።

ተገደመ ግ ገዳም ሆነ።

አስገደመ ግ ገዳም እንዲሆን አስደረገ።

*ገደመ

ገደማ ስ አካባቢ። *ወደ ሁለት ሰዓት ገደማ ይመጣል / ቤቱ ወደ ፒያሳ ገደማ ነው።*

ጋድሚያ ቅ (ስድብ) እንቅልፋም፡ ሰነፍ።

ጋድም ስ ርብራብ።

ግድም ስ ገደማ።

ተጋደመ ግ 1. ወደ ጎን በቁመቱ ተዘረጋ። 2. ተኛ።

ተገዳደመ (ነውር) የግብረ ስጋ ግንኙነት ፈፀመ።

አጋደመ ግ በቁመቱ አስተኛ፤ ዘረጋ።

አጋደመው 1. ዘረጋው፡ በቁመቱ አስተኛው። 2. ጣለው፤ ዘረረው።

አግዳሚ ስ 1. አግዳሚ ወንበር። 2. ወደጎን በቁመቱ ተዘርግቶ የሚቀመጥና ለተለያየ ግልጋሎት የሚውል (እንጨት፡ብረት፤...)።

አግዳሚ ወንበር ስ ወደ ጎን ቁመቱ ረዥም ሆኖ ብዙ ሰው ሊያስቀምጥ የሚችል ወንበር።

አግድመት ስ ሽቅብ ወይም ቁልቁል ሳይሆን በጎን በኩል የሚያስኬድ መንገድ።

አግድም ቅ ቀጥ ብሎ ሳይሆን ወደጎን። *የዛፉ አዘቃቀል አግድም ነው።*

አግድም አየ በንቀት አየ ወይም ተመለከተ።

አግድም አደግ (ስድብ) ሳይቀጣ ያደገ፡ ባለጌ።

አግድሞሽ ስ 1.አግድመት። 2. ወደ ጎን።

*ገደረ

ተገደረ ግ ታበየ፤ በኩራት ተወጠረ።

ተገዳደረ ግ 1. ዝ.ክ. 2. ተፎካከረ(እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ በማለት)።

ተግዳሮት ስ 1. ትእቢት፤ ግንአለብኝነት። 2. ሽሙጥ።

*ገደረደረ

ግድርድር(ገደርዳራ) ቅ አንድን ነገር ለማድረግ፤ ለማግኘት፡... እየፈለገ እንደማይፈልግ መስሎ የሚቀርብ፡ ፍላጎቱን የሚደብቅ ወይም አቅሙ ከሚፈቅድለት በላይ ለማድረግና ያለው ለመምሰል የሚሞክር።

ተግደረደረ ግ 1. አንድን ነገር ለማድረግ ወይም ለማግኘት እየፈለገ እንደማይፈልግ መስሎ ቀረበ፤ ፍላጎቱን ደበቀ። 2 ሳይኖረው እንዳለው መስሎ ቀረበ (ሃብት፤ ንብረት)።

ተግደርዳሪ ቅ ግድርድር።

አግደረደረ ግ 1. በልቡ እየፈለገ በአፉ አልፈልግም ወይም አላደርግም የሚልን ሰው እሺ እንዲል ደጋግሞ ለመነ፡ ጠየቀ። 2. ለተወሰነ፤ ለጥቂት ጊዜ አቆየ። *ያለኝ ገንዘብ እስከ ደመወዝ ያግደረድረኛል።*

አያግደረድርም 1. ያለው አነስተኛ ነው፡ ለብዙ ጊዜ አይበቃም። 2. አያኮራም።

ገደበ ግ 1. አገደ፤ ገታ፤ ከለከለ። 2. ወሰነ፤ ገደብ አበጀ። 3. ግድብ ሰራ፡ ከተረ።

ገደብ ስ 1. ልክ፤ መጠን፤ ወሰን(የጊዜ፤ የውለታ፤...)። 2. ማእቀብ።

ገደቡ ተነሳ ታግዶ ወይም ተከልክሎ የነበረው ነገር እንዲካሄድ፡ እንዲከናወን ተፈቀደ።

በገደብ 1. ልቅ ባልሆነ ሁኔታ፤ በውሱን (የጊዜ፤ የግንኙነት)። 2 በተወሰነ ውለታ። *ባሏ ሁለተኛ ሊጋራ ላያጨስ ቃል ገብቶ በገደብ ታረቁ።*

ግድብ ስ ውሃ መጠኑና ከፍታው ጨምሮ ጉልበት ኖሮት ለሃይድሮ ኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫነት እንዲያገለግል ወይም የውሃ እጥረት በሚኖርበት ወቅት ውሃ አጠራቅሞ ለማቆየት ሲባል ወይም ውሃ ወደ አልተፈለገ አቅጣጫ እንዳይፈስ ለማድረግ ወይም ውሃውን ለእርሻ ስራ ለማዋል በአፈር፤ በአሸዋ ወይም በድንጋይ ወይም በሲሚንቶ ተገንብቶ የሚሰራ መከለያ፤ ማገጃ፤

መከተሪያ።

ተገደበ ግ ግድብ ተሰራለት (ውሃ)።

ገደደ^{1} ግ ጠመመ፡ ዘመመ።

ገዳዳ ቅ ጠማማ፥ ወልጋዳ፥ ዘመም ያለ።

ተንጋደደ ግ ተጣመመ፡ ዘመም አለ።

አንጋደደ ግ 1. ተንጋደደ። 2. አጣመመ፡ ዘመም አደረገ።

ገደደ^{2} ግ ቸገረ። *የሱ ነገር መቼ ገደደኝ።*

ግዳጅ ስ 1. ከራስ ስሜትና ፍላጎት ውጪ በሆነ ተፅእኖ አንድን ተግባር የማከናወን ሁኔታ ። 2. በመንግስት፡ በፖለቲካ ድርጅት፡...ትእዛዝ መሰረት የሚፈፀም የጦርነት፡ የአሰሳ፡ የጥበቃ፡... እንቅስቃሴ።

ግዳጅ ሄዷል (ግዳጅ ላይ ነው) ለውጊያ ወደ ጦር ሜዳ ሄዷል።

ግዴታ ስ 1. መሆን ወይም መፈፀም ያለበት፡ የማይቀር ነገር። 2. ሃላፊነት። *ልጅን የማሳደግ ግዴታ* አለበት። 3. ግዳጅ።

ግዴታ ገባ አንድን ነገር ሊፈፅም ወይም ሊያደርግ ተዋዋለ፡ተስማማ፤ ቃል ገባ።

ግድ 1. ውዴታና ፈቃደኝነት የሌለበት። 2. መሆን ወይም መፈፀም ያለበት፡ የማይቀር፥ አስፈላጊ። *ግድ ሆኖብኝ እንጂ አልመጣም ነበር /የሱ መምጣት ግድ ነው።*

በግድ ያለፍላጎት፡ በማስገደድ።

የግዱን ሳይፈልግ፡ አማራጭ ሲያጣ።

ግድ አለ አስቸገረ፡ አስጨንቆ ያዘ። *ከሱ ጋር እንድሄድ ግድ አለኝ።*

ግድ የለም 1. የዛቻ አነጋገር። *ግድ የለም ላሁን ብታመልጠኝ በኋላ አገኝሃለሁ።* 2. ይሁን፡ ምንም አይደለም (መስማማትን፡ ቅር አለመሰኘትን ለመግለፅ)። 3. ላታስብ፡ አትጨነቅ እኔ እፈፅመዋለሁ ለማለት የሚነገር።

ግዴለሽ ቅ ችላ ባይ፥ ቸልተኛ፤ ሃሳብ የለሽ።

ተገደደ ግ ያለፍላጎቱ፤ በሃይል ወይም በትእዛዝ እንዲያደርግ ሆነ።

አስገደደ ግ ያለፍላጎት፥ በሃይል ወይም በትእዛዝ እንዲፈፅም ወይም እንዲከናወን አደረገ።

ገደገደ (ገረገደ) ግ 1. አቆመ፥ ተከለ (የእንጨት አጥርን ወይም ግድግዳን)። 2. አቆመ፡ ገተረ(ባልሆነ ቦታ ወይም ሁኔታ)። 3. ቆዳን ወጥሮ በችካል መታ።

ግድግዳ ስ ወደ ላይ ቁመት ወደ ጎን ርዝመት እንዲኖረው ተደርጎ ከእንጨት ወይም ከጡብ ወይም ከብሎኬት፥... የሚሰራ የቤት ወይም የህንፃ ጎንና ቁመት ወይም ክፍሎችን ለመከፋፈል፡ ለመለያየት ወይም አንድን ነገር ከሌላው ለመለየት የሚያገለግል መከለያ።

የግድግዳ ሰአት ስ ግድግዳ ላይ የሚሰቀል ትልቅ ሰአት።

የግድግዳ ወረቀት ስ በቤት ውስጥ ግድግዳን ለማስጌጥ ሙሉ በሙሉ ግድግዳው ላይ የሚለጠፍ ወረቀት።

ተገደገደ ግ 1. ቆመ፡ ተተከለ(የአጥር ወይም የግድግዳ እንጨት)። 2. ቆመ፡ ተገተረ (ባልሆነ ቦታ ወይም ሁኔታ)። 3. ተወጠረ(ቆዳ በችካል)።

***ገደገደ**

ገድጋዳ ቅ 1. ቀጥ ብሎና ሚዛኑን ጠብቆ መቆም ወይም መራመድ የማይችል፡ የሚወዛወዝ። 2. ፊደሎችን እየቆጠረና እየጎተተ የሚያነብ ወይም የሚናገር።

ተንገዳገደ(ተንገደገደ) ግ ቀጥ ብሎና ሚዛኑን ጠብቆ መቆም ወይም መራመድ ተሳነው፥ ተውተረተረ።

አንገዳገደ(አንገደገደ) ግ ቀጥ ብሎና ሚዛኑን ጠብቆ መቆም ወይም መራመድ እንዳይችል አደረገ፡ አውተረተረ።

ገደፈ^{1} ግ 1. ፆም ፈታ ወይም ፈሰከ ወይም ጊዜው ሳይደርስ ፆምን ሻረ፥ በላ። 2 ሲያነብ ወይም ሲፅፍ ፊደልን ወይም ቃልን ተወ፡ ዘለለ።3. በኮከብ ቆጠራ ጊዜ አንድን የተወሰነ ቁጥር ለሌላ ለተወሰነ ቁጥር አካፍሎ ቀሪውን ያዘ።

ግድፍ ቅ ተቀንሶ እንዲወገድ የተደረገ የቁጥር መጠን (በኮከብ ቆጠራ ስሌት ጊዜ)።

ግድፈት ስ በመፃፍ ወይም በማንበብ ጊዜ ፊደልን ወይም ቃልን በመርሳት ወይም በመዝለል የሚፈፀም ስህተት ወይም ሌላ ማንኛውም ስህተት።

ተገደፈ ግ 1. በንባብ ወይም በፅሁፈት ጊዜ ፊደል ወይም ቃል ተዘለለ ወይም ተተወ። 2. አንድ ቁጥር ለሌላ ቁጥር ተካፈለ (የኮከብ አቆጣጠር ስሌት)።

አገደፈ ግ እንዲፈስክ ወይም ፆም እንዲፈታ አደረገ (ምግብ በማቅረብ፥ በመስጠት)።

አስገደፈ ግ 1. ጊዜው ሳይደርስ ፆምን እስትቶ አስበላ፥ አስሻረ። 2. አገደፈ።

ገደፈ^{2} **"ደገፈ"**ን ተመ.

ገዲ "ገዴ"ን ተመ.

ገዳም "ገደመ" ስር ተመ.

ገዳም "ገድ" ስር ተመ.

ገዳይ "ገደለ" ስር ተመ.

ገዳዳ "ገደደ" ስር ተመ.

ገዴ (ገዲ) ስ ደረቱ ነጭ፥ጀርባው ጥቁር፥ ጥፍሩ ቀላፋ የሆነና እንደ እባብ፡ አይጥ፡...

የመሳሰሉትን የሚመገብ የአሞራ አይነት (ስእሉን አሞራ ስር ተመ.)::

ገድ ስ ጥሩ እድል ወይም ጥሩ አጋጣሚ::

ገድ በለኝ የሚቀጥለው አጋጣሚ፥ እንቅስቃሴ፥ … የተቃና ወይም የተሳካ እንዲሆን ጀምርልኝ (ምግብ ወይም መጠጥ በመጋበዝ ወይም የሚሸጠውን እቃ የመጀመሪያ ገገር ሆኖ በመግዛት፥…)::

ገደቢስ ቅ እድለ ቢስ::

ገዳም ቅ ጥሩ እድል የሚያጋጥመው፥ እድለኛ::

ገድል ስ 1. (ክር.) ፃድቃን ወይም ሰማእታት ስለሃይማኖታቸው የተቀበሉት ችግር፥ ፈተና፥…:: 2. ፃድቃን ወይም ሰማእታት ስለሃይማኖታቸው የተቀበሉት ችግር ፈተናና የህይወት ታሪካቸው የተፃፈበት መፅሃፍ::

ገድለኛ ቅ የሚያስገርም፥ የሚያስደንቅ፥ ተአምር፥… ስራ የሚሰራ፤ ተአምረኛ:

ገድል ተሰራ ተአምር ተሰራ ወይም ታየ::

ገድጋዳ "***ገደገደ**" ስር ተመ.

ገጀራ ስ ቆንጨራ::

ገገመ ግ (ያራዳ አነ.) ችክ አለ፤ ድርቅ አለ::

ገገማ ቅ 1. ደረቅ፥ ችኮ:: 2. ያልሰለጠነ::

***ገገመ**

ገመምተኛ(ገገምተኛ) ቅ በቅርብ ጊዜ ታሞ የነበረና እየተሻለው ወይም እየዳነ ያለ በሽተኛ::

አገገመ ግ ተሻለው፥ እየዳነ ነው (በሽተኛ)::

ማገገሚያ ስ ታሞ የነበረ ሰው በደንብ እስኪድን ድረስ የሚያስፈልገው የምግብ አይነት ወይም የሚቆይበት ቦታ::

ገገረ ግ ፈሳሽ የነበረው ነገር ረጋ፥ ጠጣር ሆነ::

ግግር ቅ 1. ፈሳሽ የነበረና ወደ ጠጣርነት የተለወጠ፥ የረጋ (ለምሳሌ ግግር በረዶ):: 2. (ዘይ.) ዝምታ የሚያበዛ::

ገጠመ ግ 1. ከደነ፥ ዘጋ:: 2. ልክክ አለ፥ በደንብ ተከደነ:: 3. ተለያይቶ የነበረውን የአንድ አካል ክፍል አያያዘ፥ ሰካ፥ አንድ አደረገ:: *የመኪናውን አካል ገጠመ::* 4. ተስማማ፥ አንድ ሆነ፥ ልክ ሆነ:: 5. ተወዳጀ፥ ጓደኛ ሆነ:: 6. አገኘ፥ ደረሰ፥ አጋጠመ:: *እንዲህ አይነት ነገር ገጥሞኝ አያውቅም::* 7. ጦርነት፥ ሙግት፥ ትግል፥ ስድብ፥… (ከተቃራኒው ወይም ከተፎካካሪው ወገን ጋር) አካሄደ:: 8.ግጥም ደረሰ:: 9. ቤት መታ(ግጥም)::

ገጣሚ ስ ግጥም የሚደርስ::

ገጠመኝ ስ ያለፈ የኑሮ ወይም የህይወት ልምድ፤ ተሞክሮ::

ግጥሚያ ስ ውድድር፥ ፉክክር(ለምሳሌ የእግር ኳስ ግጥሚያ)::

ግጥም ስ 1. ስምም ወይም አንድ መሆን:: *ከልጁ ጋር ግጥም ናቸው::* 2. ዝግ፥ ቁልፍ፥ እሽግ:: 3. በስንኝ በስንኝ እየሆነና ቤት እንዲመታ እየተደረገ የሚዘጋጅ ንግግር ወይም ፅሁፍ::

ግጥም ደረደረ ግጥም ደረሰ::

ግጥም ደርዳሪ ገጣሚ::

ግጥም አለ ግ 1. ሞላ፥ ጢም አለ:: 2. ድንገት ተገናኘ:: 3. ነፍሱ ከስጋው ተለያየ ወይም የሞተ ያህል ራሱን ሳተ::

ግጥም አድርጎ በደንብ አድርጎ:: *ግጥም አድርጎ በላ/ግጥም አድርጎ አሰረ / ግጥም አድርጎ ጠጣ::*

ግጥምጥም አለ ግ 1. ድንገት ተገናኘ:: *ዛሬ ጧት ድንገት ከድሮ ጓደኛዬ ጋር ግጥምጥም አልን::* 2. ተሳካ (ለአንድ ጉዳይ የሚያስፈልጉ የተለያዩ ነገሮች በተመሳሳይ ጊዜ በመገኘትና በመከናወን)::

ተገጣጠመ ግ 1. ድንገት ተገናኘ:: 2. አንድን የተወራ ውሸት፥ ሃሜት፥… ለማጣራት ወሬውን ወይም ሃሜቱን ካወራው ሰው ጋር የተወራበት ሰው ፊት ለፊት ተገናኝቶ ተነጋገረ:: 3. የተለያዩ ነገሮች ወይም ሁኔታዎች በተመሳሳይ ጊዜ ወይም ሁኔታ ተፈፀሙ:: 4. ተሳካ (ለአንድ ጉዳይ የሚያስፈልጉ የተለያዩ ነገሮችን በተመሳሳይ ጊዜ ማከናወን ተቻለ)::

ተገጣጣሚ ቅ ተሰካክቶ አንድ አካል የሚሆን ወይም ሊፈታቱና ሊለያዩ የሚችሉ ትናንሽ ክፍሎች ያሉት:: *ተገጣጣሚ አልጋ/ ተገጣጣሚ ቤት::*

ተጋጠመ ግ 1.ተፋለመ፥ ተዋጋ:: 2. (ስፖ.) ተወዳደረ፥ ተፎካከረ፤ ተጫወተ::

ተጋጣሚ ስ ተወዳዳሪ፥ ተፎካካሪ (በስፖርት ጨዋታዎች)::

አገጣጠመ ግ 1. አገናኘ፥ ፊት ለፊት አቀራረበ(የተወራን ሃሜት ወይም ውሸት፥… ለማጣራት ሲባል አውራውንና የተወራበትን ሰው):: 2. የ "**አጋጠመ**"ን 2ኛ ፍቺ ተመ.

አጋጠመ ግ 1. አገናኘ፥ ፊት ለፊት አቀራረበ (የተወራን ሃሜት ወይም ውሸት ለማጣራት ሲባል አውራውንና የተወራበትን ሰው):: 2. አንድ ድርጊት፥ ሁኔታ ድንገት ሆኖ ደረሰ:: *ችግር ሊገጥመው /እድል ሊገጥመው::* 3. የሞተ ሰውን ገነዘ፥ አስተካከለ (አይኑን፥ አፉን፥… በመዝጋት)::

አጋጣሚ ቅ ሳይታሰብ በድንገት የሚደርስ፥ የሚሆን፥ የሚገኝ (ጥሩ ወይም መጥፎ ነገር)::

ገጠር ስ ከከተማ ውጪ የሆነ ቦታ፤ ባላገር::

ገጠሬ ስ በገጠር ኗሪ የሆነ፣ ባላገር።

ገጠበ ግ 1. በመምለጥ ወይም በመላጥ አቆሰለ። 2. ውጣ ገባ አድርጎ ቆረጠ ወይም ሳጨ(ለምሳሌ ፀጉርን)። 3. ከመጠን በላይ ቆረጠ፥ነጨ(ለምሳሌ ሳርን)። 4. ገረፈ፣ ደበደበ፥ መታ(በአለንጋ፥ በጅራፍ፥...)።

ገጣባ ስ 1. የጋማ ከብት ጀርባ ላይ የሚገኝ ቁስል። ቅ 2. ጀርባው ላይ የተላጠ ወይም ቁስል ያለበት(የጋማ ከብት)። 3. (ስድብ) መላጣ።

ግጥብ ቅ 1. ተልጦ የቆሰለ (የጋማ ከብት ጀርባ)። 2. ሳርና ቅጠል፥... የሌለበት ወይም የተመለጠ (መሬት)።

ገጠገጠ^1 ግ በብዛት ደረደረ። *ለምትኩም ጣቶቿ ላይ ቀለበት ገጥግጣለች።*

ተገጠገጠ ግ 1. በብዛት ተደረደረ፣ ተከማቸ *ተማሪው አዳራሹ ውስጥ ተገጥግጧል።* 2. ግጥም ብሎ ሞላ፥ ጢም አለ። *አዳራሹ በሰው ተገጥግጧል።*

ገጠገጠ^2 ግ ጠባ፥ መጠመጠ (ጡትን፥ ጡጦን፥...)።

ገጠጠ ግ 1. አፈንግጦ ወይም ወደ ውጪ ወጣ ብሎ ታየ (ለምሳሌ ጥርስ)። 2. (ዘይ.) ግልፅ ሆኖ ወይም ፈጦ ታየ።

ግጣጣ ቅ 1. ጥርሱ ወደ ውጪ ወጣ ብሎ የሚታይ። 2. መሳቅ የሚያበዛ፣ መገለጢጥ።

አገጠጠ ግ 1. ገጠጠ። 2. ሳቀ፥ ገለፈጠ።

*ገጠጠ

ተንጋጠጠ ግ ወደ ላይ ቀና አለ (አንገት)።

አንጋጠጠ ግ 1. ወደ ላይ ቀና አለ፣ ወደ ሰማይ አየ። 2. አንገቱን አሰገገ፣ አረዘመ (ለማየት)።

ገጣሚ "ገጠመ" ስር ተመ.

ገጣባ "ገጠበ" ስር ተመ.

ገጣጣ "ገጠጠ" ስር ተመ.

ገጥ "ገፅ"ን ተመ.

ገጨ ግ 1.መታ፥ ለተመ፣ አላተመ። 2. የግጭት አደጋ አደረሰ።

ግጭት ስ 1. ጥል፣ ጠብ። 2. አንድ ተሽከርካሪ ሌላ ተሽከርካሪን ወይም ሰውን፥ እንስሳን፣ ንብረትን፥... በመግጨቱ የተነሳ የሚፈጠር አደጋ።

ተገጨ ግ የግጭት አደጋ ደረሰበት።

ተጋጨ ግ 1. ተላተመ፣ የግጭት አደጋ አደረሰ ወይም ደረሰበት። 2. ተጣላ።

አጋጨ ግ 1. አላተመ፣ እንዲጋጭ አደረገ። 2. መታ። 3. አጣላ፣ አራበሸ።

*ገጨገጨ

ተንገጨገጨ(ተንገጫገጨ) ግ ሲወዛወዝ ወይም ሲንቃነቅ ድምፅ አሰማ።

አንገጨገጨ(አንገጫገጨ) ግ ወዘወዘ ወይም አንቃነቀ (ለምሳሌ በኮረኮንች ላይ የሚሽከረከር መኪና)።

ገፅ (ገጥ) ስ 1. ፊት፥ መልክ። 2. በፊት በኩል (የጀርባ ተቃራኒ) ። 3. የመፅሃፍ፣ የጋዜጣ ቅጠል ወይም ወረቀት ወይም የአንድ ቅጠል ወረቀት አንደኛው ወገን።

ገፀ በረከት ስ ስጦታ፥ እጅ መንሻ፥ መታያ።

ገፀ ባህርይ ስ በልቦለድ፥ በትያትር፥...ድርሰት ውስጥ የሚገኝ ሰው(ለምሳሌ ፍቅር እስከ መቃብር በተባለው መፅሃፍ ውስጥ ከሚጠቀሱት ሰዎች መካከል ጉዱ ካሳ አንዱ ገፀ ባህርይ ነው)።

*ገፈለለ

ተንገፈለለ ግ 1. በጣም ረዥም ሆነ፥ ተንቀዋለለ። 2. ቁመቱ ከሚገባው በላይ የረዘመ ሆኖ ፍሬ ሳይዝ ቀረ (ለምሳሌ በቆሎ)።

*ገፈለፈለ

ግንፍልፍል(ግፍልፍል) ስ እየፈላ ባለ ወጥ ውስጥ እንጀራ በትላልቁ ቆረስ ቆረስ አድርጎ በመጨመርና በማደባለቅ የሚዘጋጅ ምግብ።

ተግፈለፈለ ግ 1. ተፍለቀለቀ፥ ተንተከተከ (ወጥ)። 2. ግንፍልፍል ተዘጋጀ።

አግፈለፈለ ግ 1. አፈላ፥ አንተከተከ(ወጥን፥ ግንፍልፍልን)። 2. ግፍልፍል አዘጋጀ።

ገፈራ ስ የፈረስና የበቅሎ መኖ።

ገፈተረ ግ በሃይል ገፋ፥ አሽቀነጠረ።

ገፈት(ገፈታ) በጠላ ላይ የሚንሳፈፍ የአሻሮ፥ የብቅል፥ የጌሾ ያልደቀቀው ክፍል፥ ቆርጥራጭ።

ገፈት ቀማሽ የአንድ ችግር፥ መከራ፥... የመጀመሪያው ተጠቂ፣ አሳር ቀማሽ።

ገፈታም ቅ (ስድብ) ሰካራም።

ገፈገፈ ግ ለረዥም ጊዜ ሳያቋርጥ ከፈለ(እዳን፥ ክፍያን፥...)።

*ገፈገፈ

ግፍግፍ አለ ግ ተንገፈገፈ።

ግፍግፍ አደረገ ግ አንገፈገፈ።

ተንገፈገፈ ግ ተማረረ፥ ተንገሸገሸ፥ ሰለቸ።

አንገፈገፈ ግ አንገሸገሸ፥ አሰለቸ።

*ገፈጠጠ

ግፍጥጥ(ገፍጣጣ) ቅ (ስድብ) ሆዱ የተንዘረጠጠ ወይም ትልቅ የሆነ።

ግፍጥጥ አለ ግ ተንገፈጠጠ።

ግፍጥጥ አደረገ ግ አንገፈጠጠ።

ተንገፈጠጠ ግ ተንዘረጠጠ ወይም ትልቅ ሆነ (ሆድ)።

አንገፈጠጠ ግ አንዘረጠጠ (ሆድን)።

እንግፍጥ ቅ ሆዱ የተንዘረጠጠ።

ገፈፈ ግ 1. ቆዳን ከሲጋ ለየ። 2. ልብስን ከሰውነት ላይ አነሳ። 3. ቀማ፥ ዘረፈ። 4. ሰቀቀ፤ ደበዘዘ(ቀለም)። 5. ገለጠ(ዳመና)።6. ስልጣንን ወይም ማእረግን ቀማ፤ ሻረ።

ገፈፋ ስ ዝርፊያ፥ ቅሚያ።

ገፋፊ ቅ ቀማኛ፤ ዘራፊ።

ገፋ ግ 1. ገፈተረ፤ ወረወረ። 2.ፎቀቅ አደረገ፥ወደፊት አስጠጋ። 3. ናጠ፥ ወዘወዘ (ወተት ያለበትን እቃ)።4. ወደ ፊት አመራ፥ ሄደ። 5.እየተሰራ ወይም እየተከናወነ ሄደ (ስራ)። 6.እየጨመረ ወይም እየተለቀ ሄደ(ሆድ)። 7.ረዘመ። *ክረምቱ ገፋ*። 8. በደለ፥ አንገላታ። 9. ጨመረ። *እድሜው እየገፋ ሄደ*።

ገፍቶ መጣ ሳይፈለግ በራሱ መንገድና ሁኔታ ሆነ ወይም መጣ።

ግፋ ቢል ቢበዛ፤ ቢጨምር፥ የባሰ ቢመጣ።

መግፈያ ስ የወተት መናጫ።

ገፊ ቅ አደጋ ወይም ችግር የደረሰው እሱ በአካባቢው በመኖሩ ወይም በመገኘቱ ምክንያት ነው ተብሎ የሚታመንበት ነገር ወይም ወሳኙ፤ ዘመዶቹ፥... በሞት አልቀውበት ብቻውን የቀረ ፤ ገዳ ቢስ ።

ግፊያ ስ ከሰው ብዛትና ከመጋፋት የተነሳ የሚፈጠር ትርምስ፤ ትንቅንቅ።

ግፊት ስ ጉትጎታ፥ ተፅእኖ። *ንቅናቄው የውጭ ግፊት አለበት*።

ግፍ ስ አንዱ በሌላው ላይ የሚያደርሰው ወይም የሚፈፅመው በደል፤ ክፉ ስራ።

ግፍ ዋለ ክፉ አደረገ፥ ግፍ ሰራ፥ በደል ፈፀመ።

ግፈኛ ቅ እቅም አለኝ ብሎ ሌላን የሚበድል፥ ግፍ የሚሰራ።

ገፋፋ ግ በል በል አለ፤ አበረታታ፤ ጎተጎተ (አንድን ድርጊት እንዲፈፅም)።

ተገፋ ግ በደል ወይም ግፍ ደረሰበት።

ተገፋፋ ግ በል በል ወይም አድርግ አድርግ ተባለ፤ ተበረታታ፤ ድፍረት አገኘ(አንድ ድርጊት እንዲፈፅም)።

ተጋፋ ግ 1. ተቀናቀነ፥ ተዳፈረ። *ስልጣን ተጋፋ*። 2. ትርምስ ወይም ትንቅንቅ ባለበት ቦታ ገብቶ ከመጣበብ የተነሳ ተገፈታተረ።

አጋፋ ግ እንዲጋፋ ምክንያት ሆነ።

ገፋፊ "ገፈፈ" ስር ተመ.

ገፋፋ "ገፋ" ስር ተመ.

ገፍ ቅ ብዙ። *ዘንድሮ ዝናቡ ገፍ ነው*።

በገፍ በብዛት።

ገፍጣጣ "ገፈጠጠ" ስር "ግፍጥጥ"ን ተመ.

ጉ የ "ገ" ፊደል ካእብ ዘር።

ጉለንታ "ጎለንታ"ን ተመ.

ጉሊት[1] ስ 1.ያልደቀቀ አፈር፤ ጓል። 2. በምስጥ የተሰራ ጉብታ።

ጉሊት[2] "ጎለተ" ስር "ጉልት"ን ተመ.

ጉላንጅ ቅ 1. በቀላሉ የማይታኘክ፤ መንቻካ ስጋ።2. (ዘይ.፡ ስድብ) ፀባዩ መጥፎ የሆነ፤ ችኮ።

ጉል "ጓል"ን ተመ.

ጉልህ "ጎላ" ስር ተመ.

ጉልላት ስ ብዙውን ጊዜ ክብ ሆኖ በተሰራ ቤት ወይም በቤተክርስቲያን አናት ላይ የሚደረግ ድቡልቡል ወይም ክብ ወይም የአክሊል ወይም የዘውድ ቅርፅ ያለውና ከቆርቆሮ ፥ ከሸክላ፥... የሚሰራ ጌጥ።

ጉልማ "ጎለመ" ስር ተመ.

ጉልምስና "ጎለመሰ" ስር ተመ.

ጉልበተኛ "ጎለበተ" ስር ተመ.

ጉልቢታም ዝ.ክ.

ጉልበት ዝ.ክ.

ጉልባን ስ የባቄላ ክክ ከስንዴ ወይም ከተፈተገ ገብስ ጋር አንድ ላይ ተቀቅሎ የሚዘጋጅና የፀሎተ ሃሙስ እለት የሚበላ ንፍሮ።

ጉልት ስ ቀደም ባለው ጊዜ ከንጉስ ይሰጥ የነበረ ርስት።

ጉልተኛ ቅ ባለጉልት።

ጉልት "ጎለተ" ስር ተመ.

ጉልቻ ዝ.ክ.

ጉልድም "ጎለደመ" ስር ተመ.

ጉልድፍ "ጎለደፈ" ስር "ጎልዳፋ"ን ተመ.

ጉልጎላ(ጉልጓሎ) "ጎለጎለ" ስር ተመ.

ጉልጥምት ስ 1. የጉቶ ቂጥ። 2. የቅልጥም ጫፍና ጫፍ፥ የአጥንት ራስ።

ጉሎ(ቃጭማ) ስ ቅጠሉ ሰፋፊ የሆነና ፍሬው ዘይት የሚወጣው የእፅዋት አይነት።

የጉሎ ዘንግ (ዘይ.) ተንኮል የሌለው፥ አቅመ ቢስ።

የጉሎ ዘይት ስ ከጉሎ ተክል ፍሬ የሚዘጋጅ ዘይት።

ጉመሮ(ገመሮ) ስ ፍሬው የሚበላ፥ እንደ ሃረግ በዛፍ ላይ የሚጠመጠምና እሾህ ያለው የእፅዋት አይነት።

ጉመደው ስ እንስሳትን የሚገድል የበሽታ አይነት።

ጉማ^1 ስ ሰው የገደለ ሰው ለሟች ወገን የሚከፍለው የገንዘብ ካሳ ወይም የነፍስ ዋጋ።

ጉማ^2 ቅ ቁራጭ፡ ሙዳ (ስጋ)።

ጉማምላ ስ በባህር ዳርቻ የሚበቅል ቀላ ያለና አንጓ ያለው የእፅዋት አይነት።

ጉማሬ ስ ቆዳው በጣም ወፍራምና ፀጉር አልባ የሆነ ትልቅ ጭንቅላት አጭር ጭራና አጫጭር እግሮች ያሉት በወንዝ ወይም በባህር ውስጥ ወይም አቅራቢያ የሚኖር ግዙፍ ሳር በል እንስሳ።

ጉማሬ

ጉማሬ አለንጋ ስ ከጉማሬ ቆዳ የሚሰራ አለንጋ፤ አለርባጅ።

ጉም ስ አብዛኛውን ጊዜ በክረምት ወራት የሚታይና አልፎ አልፎ ወደታች በመውረድ የምድርን አካል ለተወሰነ ጊዜ የሚሸፍን የተነደፈ ጥጥ የሚመስል ደመና።

ጉም ለበሰ በጉም ተሸፈነ፥ ተከለለ።

የጉም ሽንት ስ 1. ከጉም ውስጥ የሚንጠባጠብና ምድርን የሚያረጥብ የዝናብ ነጠብጣብ። 2. (ዘይ.) የማይጨበጥ፡ ሾላካ (ሰው)።

የጉም ጅብ ስ 1. አካባቢው በጉም በሚሸፈንበት ጊዜ በጉሙ ውስጥ ሳይታይ በመምጣት ቀን በቀን ከብቶችን የሚበላ ጅብ። 2. (ዘይ.) ስስታም፡ ሆዳም።

ጉምሩክ ስ እቃዎች ወደ ሃገር ውስጥ ሲገቡና ከሃገር ሲወጡ ቀረጥ የሚያስከፍልና ወደ ሃገር እንዳይገቡ ወይም ከሃገር እንዳይወጡ የተከለከሉ ነገሮችን የሚቆጣጠር የመንግስት አካል።

ጉምድ "ጎመደ" ስር ተመ.

ጉምጉምታ "*ጎመጎመ" ስር ተመ.

ጉማጅ "ጎመደ" ስር ተመ.

ጉረሮ "ጉሮሮ"ን ተመ.

ጉረኖ ስ የፍየልና የበግ ማጎሪያ፥ ማደሪያ።

ጉራ ስ የሌለውን አለኝ፥ የማያውቀውን አውቃለሁ፡ የማይችለውን እችላለሁ ወይም እፈፅማለሁ የማለት ወይም ያለውን፡ የሚያውቀውን፥ የሚችለውን፥ የሚሰራውን፥ ...አጋኖ በማውራት የሚቀርብ የዝና ፍለጋ ንግግር ወይም ድርጊት።

ጉራውን ቸረቸረ / ነሰነሰ / ነዛ/ ነፋ/ ስለአለው ሃብት፡ እውቀት፡ ችሎታ፥... በማጋነን አወራ ወይም የሌለውን አለኝ፡ የማያውቀውን አውቃለሁ፥ የማይችለውን እችላለሁ፣... አለ።

ጉረኛ ቅ የሌለውን አለኝ፥ የማያውቀውን አውቃለሁ፤ የማይችለውን እችላለሁ፡ የማያደርገውን አደርጋለሁ የሚል ወይም ስለሃብቱ፥ ስለእውቀቱ፥ ስለችሎታው፥... አጋኖ የሚያወራ።

ጉራማይሌ ስ 1. ሙሉ በሙሉ ሳይሆን አለፍ አለፍ ብሎ የሚነቀስ የጥርስ ንቅሳት አይነት። 2. የተለያዩ ቋንቋዎችን በማደባለቅ የሚቀርብ ድብልቅ ንግግር ወይም ፅሁፍ (ለምሳሌ የእንግሊዘኛ ቃላት እየተደባለቁበት የሚቀርብ የአማርኛ ንግግር)። 3. ቅይጥ፥ ድብልቅ።

ጉራንጉር ስ እንደልብ ለመተላለፍ የማያመች፡ ጠባብና ወጣ ገባ የሆነ ስፍራ።

ጉራጅ "ጎረደ" ስር ተመ.

[የ]ጉራጌ ጎመን ስ ቅመሙ ረዘም ያለና ቅጠሉ ሰፋፊ የሆነ የጎመን አይነት።

ጉሬዛ ስ ከጦጣና ከዝንጀሮ ወገን የሚመደብ፥ ጢሙና ከትከሻው ጀምሮ በግራና በቀኝ በኩል ያለው አካሉ ነጭ ፤ ከአናቱ ጀምሮ እስከ ወገቡ ደግሞ ጥቁር የሆነ፡ ዙሪያው ብትን ያለ ነጭ ፀጉር የከበበው ጥቁር ጅራቱ ነጭ የሚበዛበት ወይም ጫፉ ላይ ብትን ያለ ነጭ ፀጉር ያለበት፡ ጥቅጥቅ ባለ ጫካ ውስጥ ውሃ አጠገብ በሚገኙ ረጃጅም ዛፎች ላይ የሚኖርና ካንዱ ዛፍ ወደ ሌላ በረጅሙ እየተምዘገዘገ መዝለል የሚችልና ጦጣ የሚያክል የዱር እንስሳ (ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።

ጉሬዝማ ቅ ጉሬዛ የሚመስል፤ የነጭና የጥቁር ድብልቅ መልክ ያለው።

ጉር ስ ድንጋይ የበዛበት ወይም ድንጋያማ የሆነ መሬት።

ጉርምርምታ "*ጎረመረመ" ስር ተመ.

ጉርምስና "ጎረመሰ" ስር ተመ.

ጉርሻ "ጎረሰ" ስር ተመ.

ጉርብትና "*ጎረበተ" ስር ተመ.

ጉርና ስ የወተት ማጠራቀሚያና መናጫ እቃ።

ጉርና ሆድ (ስድብ) ቀበደድ፡ ቋፈታም።

ጉርናት "ጎረና" ስር ተመ.

ጉርዝኝ ስ መጠኑ በእንቅብና በቁና መካከል የሆነ ለእህል መስፈሪያ የሚያገለግል የስፌት እቃ።

ጉርዳ ስ ላም እንዳታረግዝ የሚያደርግ የማህፀን ችግር።

ጉርዳ ሆነች አልወልድ ያለች ላም ማህፀኗን ዘግቶ እንዳታረግዝ የከለከላት ችግር በጉርዳ በሺ እንዲወገድላት ተደረገ።

ጉርዳ በሺ ስ አልወልድ ያለች ላም ማህፀን ውስጥ እጅን በማስገባት እንዳታረግዝ የከለከላትን ችግር የሚያስወግድ ወጌሻ ወይም ባለሙያ።

ጉርድ "ኀረደ" ስር ተመ.

ጉርዳሽ ዝ.ክ.

ጉርጥ ስ በአብዛኛው በመሬት የሚኖርና በመራቢያው ወቅት ውሃ ውስጥ የሚቆይ፣ ቆዳው ሻካራ የሆነ የእንቁራሪት አይነት።

ጉርጥ አይን ቅ(ስድብ) አይነ ፈጣጣ።

ጉርጥርጥ "ኀረጠ" ስር ተመ.

ጉርጉጭታ "ኀረኀጨ"ስር ተመ.

ጉሮሮ(ጉረሮ) ስ ለመተንፈሻና ምግብን ወደ ሆድ ለማውረጃ የሚያገለግል አሸንዳ መሰል ውስጣዊ የሰውነት ክፍል።

ጉሮሮው እስኪሰነጠቅ ጮሀ በጣም ጮሀ።

ጉሮሮው ደረቀ በጣም ተጠማ።

ጉስር "ኀሰረ" ስር ተመ.

ጉስቁል "ኀሰቆለ" ስር "ኀስቋላን" ተመ.

ጉስጉሻ "ጉሽጉሻ"ን ተመ.

ጉሽ "ኀሸ" ስር ተመ.

ጉሽርጥ(ግሽርጥ) ስ ስሩ ተፍቆና ደቆ ከተቀቀለ በሂላ ሴቶች እጅና እግራቸውን ለማቅለም ወይም ለማስጌጥ የሚቀቡት እንሶስላ የሚመስል የእፅዋት አይነት።

ጉሽጉሽ (ጉስጉሻ) ስ ከጭቃ የሚሰራ የእህል ማስቀመጫ፣ ድብኝት።

ጉበት ስ ለስላሳ ያለና ጥቁር ቀይ ቀለም ያለው፣ ሃሞት የሚያመነጭና ደምን የሚያጣራ፣ በሆድ እቃ ውስጥ የሚገኝ የሰውነት ክፍል።

ጉበን ስ ከመዝጊያ አናት በላይ የሚገኝ የበር አግዳሚ፣ የደፍ ተቃራኒ (ስእሉን ቤት ስር ተመ.)።

ጉባ^1 ስ ኮረብታ፣ ቀልቀታ፣ ጉብታ።

ጉባ^2 ስ የማጭድ ቅርፅ ያለው የከብት ቆስል መተከሻ።

ጉባኤ ስ 1. በአንድ ጉዳይ ላይ ለመወያየት ወይም ለመነጋገር የሚደረግ ስብሰባ።2. የተወሰኑ ጉዳዮችን እንዲያከናውኑ፣ ደንቦችን እንዲያወጡ፣ የማማከር ስራ እንዲሰሩ ተመርጠው ወይም ተሹመው የሚሰሩ ሰዎች ስብሰብ።3.አንድ ጉዳይ ላይ ለመወያየት ወይም ለመነጋገር የተጠራ ተሰብሳቢ በአንድነት የሚገኝበት መድረክ።

ጉብ

ጉብታ ስ ከፍታነት ያለው ቦታ፣ ኮረብታ።

ጉብ አለ ግ 1. ከአካባቢው ከፍ ብሎ ታየ። 2. ቁብ ብሎ ተቀመጠ፣ ጉች አለ።

ጉብራት "ኀበረ" ስር ተመ.

ጉብር ዝ.ክ.

ጉብታ "ጉብ" ስር ተመ.

ጉብኝት "ኀበኘ" ስር ተመ.

ጉብዝና "ኀበዘ" ስር ተመ.

ጉብጉባት "*ኀበኀበ' ስር ተመ.

ጉብጉብ "*ኀበኀበ" ስር ተመ.

ጉቦ ስ ህጋዊም ሆነ ህጋዊ ያልሆነን ጉዳይ ለማስፈፀም ህጋዊ ባልሆነ መንገድ የሚሰጡት ወይም የሚቀበሉት ገንዘብ ወይም ሌላ የአይነት ስጦታ፣ መማለጃ።

ጉቦ በላ ጉቦ ተቀበለ ወይም ወሰደ።

ጉቦኛ ቅ ጉቦ ካልተሰጠው ጉዳይ የማይፈፅም።

ጉተና "ኀተነ" ስር ተመ.

ጉትት "ኀተተ" ስር 'ኀታታ'ን ተመ.

ጉትቻ ስ ከወርቅ ወይም ከብር ወይም ከነሃስ፣... የሚሰራ የጆሮ ጌጥ።

ጉትያ ስ ቀንጮ።

ጉቶ ስ 1. ዛፍ ተቆርጦ ከስሩ በኩል የሚቀረው የዛፍ ጉማጅ። ቅ 2. (ዘይ.) በጣም አጭር ሆኖ ወፈር ያለና ብዙ የማይንቀሳቀስ (ሰው)።

ጉቶ ፊት ቅ (ስድብ) ፊቱ ድርቅጭ ያለ፣ ቁንጋ።

ጉች

ጉች አለ ግ 1. ከአካባቢው ተለይቶ ከፍ ወይም ጉብ ብሎ ታየ። 2. ቁጭ አለ።

ጉች ጉች ያለ ጡት ስ ደረት ላይ ፈርጠምና ቀጥ ብሎ የሚታይ የሴት ጡት።

ጉኒና ስ ከተፈተለ የበግ ፀጉር ወይም ከሳር ወይም ከሰሌን፣... የሚሰራ፣ መሃሉ ላይ ጉትያ የሚመስል ነገር ያለበትና ብዙውን ጊዜ እረኞች የሚያደርጉት ቆብ።

ጉንቁል "ኀነቆለ" ስር ተመ.

ጉንብስ "*ኀነበሰ" ስር "ኀንባሳ"ን ተመ.

ጉንዳን ስ በህብረት የሚኖር፣ ወደ ጥቁረት የሚያደላ መልክ ያለው መጠኑ ከቁንጫ ከፍ የሚል ተናካሽ የነፍሳት አይነት።

ጉንዳን

ጉንዳን ነው በጣም ብዙ ነው።*የመጣው ሰራዊት ጉንዳን ነው።*

ጉንድል "ኀነደለ" ስር "ኀንዳላ"ን ተመ.

ጉንድሽ "ኀነደሸ" ስር ተመ.

ጉንዶ ስ ከቀንድ ወይም ከግንድ ተፈልፍሎ የሚሰራ ጥንታዊ የማር መስፈሪያ::

ጉንጉን " ጎነጎነ" ስር ተመ.

ጉንጫም "*ጎነጨ" ስር ተመ.

ጉንጮ ዝ.ከ.

ጉንፋን ስ በመጥፎ ሽታ ወይም በብርድ ምክንያት የሚመጣ፡ የሚያስነጥስና የሚያስል፡ አክታና ንፍጥ የሚያስከትል የአጭር ጊዜ በሽታ::

ጉንፋኑ በሰለ የጉንፋን ህመሙ እየቀለለ መጣ፥ ለመዳን ተቃረበ::

ጉንፋናም ቅ የጉንፋን በሽታ በተደጋጋሚና በተከታታይ የሚይዘው::

ጉንፍ "ጎነፈ" ስር ተመ.

ጉኝር "ጎኘረ" ስር ተመ.

ጉዝጓዝ "ጎዘጎዘ" ስር ተመ.

ጉዞ "*ጓዘ" ስር ተመ.

ጉያ ስ 1. በጭኖች መሃከል ወይም በብብት አካባቢ ያለው የሰውነት ክፍል::2. እቅፍ:: *ልጇን በጉያዋ ይዛለች*:: 3. ከለላ፡ ጥበቃ፥ እንክብካቤ:: *በአባቱ ጉያ ስር እየኖረ ምን ይነካዋል* ?

ጉደኛ "ጉድ" ስር ተመ.

ጉዳም ዝ.ከ.

ጉዳተኛ "ጎዳ" ስር ተመ.

ጉዳት ዝ.ከ.

ጉዳይ ስ 1. አንድ መፈፀም ወይም መከናወን ያለበት ስራ ወይም ተግባር:: 2. ከአንድ የተወሰነ ነገር፥ ቦታ፥ ሁኔታ፥ ሰው፥...ጋር የተያያዘ ነገር:: *የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት*::

ባለጉዳይ ቅ 1. ጉዳይ ያለበት ሰው ወይም አንድ የሚፈልገው ነገር እንዲፈፀምለት ወደሚመለከተው ቦታ ሄዶ የሚጠይቅ ወይም የሚያመለክት ፥ የሚከታተል:: 2. ነገሩ የሚመለከተው ወይም የሚያገባው::

ከጉዳይ አልጣፈውም ትኩረት አልሰጠውም፥ አላሳሰበውም፥ አላስጨነቀውም::

ጉዳዩ አይደለም 1.ግድ አይሰጠውም፥ አያስጨንቀውም:: 2. አይመለከተውም::

ጉዳይ አስፈፃሚ /ፈፃሚ ቅ 1. ከአንድ የተወሰነ ስራ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ለማስፈፀም ተቀጥሮ የሚሰራ:: ስ 2. አምባሳደር ባልተሾመበት ኤምባሲ ውስጥ የአምባሳደሩን ቦታ ተክቶ የሚሰራ ሰው፥ ዲፕሎማት::

—ጉዳይ ስ.የሚቀረው ወይም የሚጎድለው (ብዙውን ጊዜ ለሰአት):: *ለሰባት ሩብ ጉዳይ*:

ጉድ ስ 1. የሚያሳዝን ወይም የሚያሳፍር፥ የሚያስደንቅ ድርጊት ወይም ሁኔታ:: 2. ያልተለመደ፤ እንግዳና አስገራሚ ነገር:: 3. መጥፎን ወይም ጥሩን ነገር ለማድነቅ የሚነገር ቃል::

ለጉድ የጎለተው ችግር ወይም መከራ እንዲያይ እድሜው የረዘመ::

ጉድ ሆነ መጥፎ ነገር፥ ችግር፥... አጋጠመው::

ጉድ ታየ የሚያስገርም ወይም የሚያስደንቅ ነገር ታየ::

ጉድ አወጣ ምስጢርን ወይም የተደበቀን ነገር አወጣ፥ አጋለጠ::

ጉድ አደረገው 1. የሚጎዳ ነገር፥ ችግር፥... አደረሰበት:: 2. አዋረደው ወይም አጭበረበረው::

ጉድ ፈላ ያልታሰበ ወይም ያልተጠበቀ ድንገተኛ ነገር ደረሰ::

ጉደኛ ቅ 1. ድርጊቱ ሁሉ አስገራሚ ወይም አስደናቂ የሆነ፤ተአምረኛ:: 2. በጣም የሚያምር፥ ቆንጆ:: *ጉደኛ ቤት አለው*::

ጉዳም ቅ እንዳይታወቅበት የሚፈልገውና የሚሸሸገው ነገር ያለበት (ሰው)::

ጉድኝ ስ በደጋ አካባቢ ውሃማ በሆነ ቦታ ላይ የሚበቅልና የሚበሉትን እንስሳት ሊገድል የሚችል አነስተኛ የእፅዋት አይነት::

ጉድጉድ

ጉድጉድ አለ ግ 1. በቤት ውስጥ ወዲያ ወዲህ አለ(ምግብ ለማብሰል፤ለማቅረብ ወይም ቤት ለማዘጋጀት፡ ለማፅዳት፥... ወይም እቃን ለመፈለግ):: 2. በቤት ውስጥ ምግብ ሲያበስል ወይም እቃ ሲያዘጋጅ ወይም ሲፈልግ፥... የኮቴ ድምፅ አሰማ::

ተንጎዳጎደ ግ 1. ጉድጉድ አለ:: 2.(ዘይ.) በድብቅ የግብረ ስጋ ግንኙነት ፈፀመ፤ ተልከሰከሰ::

አንጎዳጎደ ግ 1. የ"ጉድ ጉድ አለ"ን 2ኛ ፍቺ ተመ. 2.በድብቅ የግብረ ስጋ ግንኙነት ፈፀመ፤ተልከሰከሰ::::

ጉድለት "ጎደለ" ስር ተመ

ጉድባ "ጎደበ" ስር ተመ.

ጉድጓድ "ጎደጎደ" ስር ተመ

ጉድፍ "ጎደፈ" ስር ተመ.

ጉዶ ስ እንደ ጎራዴ ያለ ሆኖ ከጎራዴ አጠር ያለ ያለ ማረጃ::

ጉጉ "ጓጓ" ስር ተመ.

ጉጉት^{1} ስ ክብ ፊትና ትላልቅ አይኖች ያሉት፥ በቀን ብርሃን ማየት ስለማይችልና በጨለማ ጊዜ ብቻ የሚዘዋወር የአሞራ አይነት (ስእሉን አሞራ ስር ተመ.)::

ጉጉት^2 "ጓጓ" ስር ተመ.

ጉጉግ ስ መልኳ ቡኒና ነጭ የሆነ፥ የእግሯ ጣት እንደ ጃንጥላ ቅድ ሆኖ የተያያዘና በውሃ አጠገብ የምትኖር የአሞራ አይነት።

ጉግስ ስ አባራሪና ተባራሪ በመሆን ፈረሰኞች ዘንግ እየወረወሩ በመወጋጋትና በመመከት የሚጫወቱት የባህል ጨዋታ።

ጉጠት ስ 1. ብዙውን ጊዜ ብረት ቀጥቃጮች የጋለ ብረትን ለመያዝ የሚጠቀሙበት እንደ መቆንጠጫ ያለ መንታ ጫፍ ያለው ብረት። 2. ለመንቀል ወይም ምስማርን ሰርስሮ ለማውጣት የሚያገለግል ጫፉ ቆልመም ያለ ብረት።

ጉጥ "*ጎጠጎጠ" ስር ተመ.

ጉጥር "ጎጠረ" ስር ተመ.

ጉጭማ ስ 1. እባቂ (የዶማ)። 2.(ስድብ) ቁመቱም ሆነ አንገቱ አጭር የሆነና ወፈር ያለ ሰውነት ያለው (ሰው)።

ጉፋያ "ጎፈየ" ስር ተመ.

ጉፍታ ስ ብዙውን ጊዜ ሙስሊም ሴቶች ፀጉራቸውን እስከ አንገታቸው ድረስ የሚሸፍኑበት ሻሽ።

ጉፍጥጥ "ጎፈጠጠ" ስር "ጎፍጣጣ"ን ተመ.

ጊ የ"ገ" ፊደል ሳልስ ዘር።

ጊርጊራ "ግርግራ^1"ን ተመ.

ጊታር ስ እንደክራር እየመቱ የሚጫወቱበት የክር ዘመናዊ ሙዚቃ መሳሪያ(ስእሉን የሙዚቃ መሳሪያ ስር ተመ.)።



ጊንጥ ስ 1. በእንጨት ቅርፊትና በድንጋይ ስር የምትኖር፥ ጅራቷ ረዥም ሆና ክርክር ያለውና ተናዳፊ መርዘኛ ነፍሳት። ቅ 2. (ዘይ.) ክፉ፥ መርዘኛ።

ጊዜ ስ 1. ከአለፈው እስካሁን ያለው ወደፊትም የሚመጣው ሰከንድ፥ ሰአት፥ ቀን፥ ሳምንት፥ ወር፥ አመት። 2.ከመምሸቱ ትንሽ ቀደም ብሎ ያለው ሰአት ወይም ወቅት። 3. አንድ ነገር የሚሆንበት ወይም የሚፈፀምበት ወይም የሚገኝበት ወይም የሚሰራበት ተገቢ ወቅት ወይም ሰአት። *ለሁሉም ጊዜ አለው።*

ለጊዜው ለአሁኑ፥ በቋሚነት ሳይሆን።

በ___ ጊዜ ___ በነበረበት ወቅት፥ ዘመን። *በንጉሱ ጊዜ።*

በየጊዜው ዘወትር፥ ሁልጊዜ።

በጊዜ 1. ሰአቱ ከመድረሱ በፊት፥ ቀደም ብሎ። *ከቀጠሮው በፊት በጊዜ ደረሱ።* 2.በጣም ሳይመሽ። *ሊያመሽም ወደ ቤቱ በጊዜ ይገባል።*

በጊዜው በዘመኑ ፡ በሰአቱ ።

ባለጊዜ ቅ ወቅቱ የፈቀደለት ወይም የተመቻቸለት፣ ባለመብት።

ከጊዜ ወደ ጊዜ ከእለት ወደ እለት፥ ከቀን ወደቀን። *ከጊዜ ወደጊዜ ሁኔታው እየተቀየረ መጣ።*

ያለጊዜው ወቅቱ ወይም ሰአቱ ሳይፈቅድ ወይም ሳይደርስ።

ጊዜ ሰጠ 1. ታገሰ። 2. ሰአት በማራዘም ፋታ ሰጠ።

ጊዜ አጠፋ ያለአግባብ ጊዜ እንዲያልፍ ወይም እንዲያልቅ አደረገ።

ጊዜ ወሰደ ብዙ ሰአት ፈጀ፥ አቆየ።

ጊዜ የለኝም በስራ ወይም በሌላ ጉዳይ ስለተያዙ ተጨማሪ ነገር የማከናውንበት ሰአት የለኝም።

ጊዜ የሰጠው ባለጊዜ።

ጊዜ የወለደው ዘመን ያመጣው።

ጊዜ ያለጊዜ 1. በምሽት። 2. አመቺ ወይም ተስማሚ ባልሆነ ወቅት፣ አጉል ጊዜ።

ጊዜ ያለፈበት ዘመኑ ያለፈ ወይም ዘመናዊ ያልሆነ።

ጊዜ ይቆጥባል ብዙ ሰአት አይፈጅም፥ ይፈጥናል ወይም ያፋጥናል።

ጊዜ ገዛ ሰበብ ፈጥሮ ጊዜን በማራዘም አንድን ነገር ለማከናወን የሚያስችለውን ሁኔታ ፈጠረ ወይም አመቻቸ።

ጊዜ ገደለ ጊዜ አጠፋ።

ጊዜ ጠበቀ አመቺ ወይም ተስማሚ ጊዜ እስኪያገኝ ቆየ።

የጊዜ ሰሌዳ ስ ስራዎች የሚከናወኑበትን ሰአት ወይም ወቅት የሚጠቁም ሰንጠረዥ።

ጊዜያዊ ቅ ለአጭር ጊዜ የሚቆይ ወይም ቋሚ ያልሆነ።

ጊዜያዊ ሰራተኛ ስ 1. የሙከራ ጊዜውን ያልጨረሰ አዲስ ሰራተኛ።2.በቋሚነት ያልተቀጠረ ሰራተኛ።

ጊደር ስ ለመጠቃት የደረሰች እንስት የቀንድ ከብት።

ጊድራ ስ 1. ክፋት፣ ተንኮል። 2. ምቀኝነት።

ጊድረኛ ቅ ክፉ፥ ተንኮለኛ።

ጊጋር ስ እንደወረንጦ ያለ መቆንጠጫ(የአንጥረኛ እቃ)።

ጊጤ ስ ሹል ዘንግ ወይም ጦር፡... እየወረወሩ በመውጋት የውድድር ጨዋታ የሚያደርጉበት የእንዶድ ወይም የሬት ግንድ፤ ጨዋታውም ጊጤ

እየተባለ ይጠራል።

ጋ^{1} የ'ግ' ፊደል ራብእ ዘር።

ጋ^{2} በስምና በተውላጠስም መጨረሻ እየገባ በታች፥ ዘ___ አጠገብ መገኘትን፣ ወይም አንድ ነገር የት እንደሚገኝ የሚያመለክት ቃል። *ጠረጴዛው ጋ /ሱሉ ጋ/ እዚያ ጋ።*

ጋ^{3}

ጋ አለ ግ የመጋጨት ድምፅ አሰማ፣ ጓ አለ።

ጋለ ግ 1. ሞቀ፥ተኩሰ፣ ጠበረረ። 2. ደመቀ፣ ሞቀ። *ጨዋታው ጋለ።*

ግለት ስ ሙቀት፤ ትኩሳት፣ ግመት።

ጋል ጋል አለ ግ ቀጣ ቀጣ አለ።

ተጋጋለ ግ ተሟሟቀ (ወሬ፥ጥል፥ ክርክር፥...)።

አጋጋለ ግ አሟሟቀ፥ አጻመቀ፥ አባባሰ (ወሬን፥ጥልን፥ክርክርን)።

***ጋለለ**

ጋለል አለ ግ ከእንግትና ከትከሻው ወደ ኋላ ዘንበል፥ ደገፍ ብሎ ተኛ፥ ጋደም አለ።

ጋለል አደረገ ግ አንጋለለ።

ተንጋለለ ግ በጀርባው ተኛ፥ ተጋደመ።

አንጋለለ ግ በጀርባው አስተኛ፣ አጋደመ።

እንግሊላ(እንግላል) ስ የጀርባ መኝታ።

ጋለሎ "*ገለለ" ስር "ግላሎ"ን ተመ.

ጋለሞታ "ገለሞተ" ስር ተመ.

ጋለበ ግ 1. በፈረስ ላይ ተቀምጦ በግልቢያ ሄደ። 2. እየፈጠነ፥ እየሮጠ ሄደ። 3. ጠለቅ ብሎ ወይም በደንብ ሳይሆን ላይ ላዩን በጥድፊያ አነበበ፥ አየ፥...።

ግልቢያ ስ 1. የፈረስ ሩጫ ወይም በሚሮጥ ፈረስ ላይ ተቀምጦ የሚደረግ የፍጥነት ጉዞ።

ጋመ ግ1. ጋለ፥ ተኮሰ(ሸክላ፥ብረት፥...)። 2.ፋመ።

ግመት ስ ግለት፥ ሙቀት።

ተጋጋመ ግ ተፋፋመ፥ ተያያዘ (እሳት፥ ጦርነት፥...)።

አጋጋመ ግ አሟሟቀ፣ አባባሰ፣ አቀጣጣለ (እሳትን፣ ጦርነትን፣...)

ጋመረ ግ አደገ፥ ጎረመሰ።

ጋመረች ግ ለአካለ መጠን ደረሰች።

ጋሙድ ስ ረሃብ።

ጋሙዳ ቅ ረሃብተኛ።

ጋማ ስ የበቅሎ፣ የፈረስ፥ የአንበሳ፥... የማጅራት ፀጉር።

የጋማ ከብት ስ እንደ ፈረስ፥ በቅሎ፥ አህያ ያሉት የቤት እንስሳት የወል መጠሪያ ስም።

ጋሜ ስ 1. መሃሉ ተላጭቶ ዙሪያውን የሚቀር የሴት ልጅ ፀጉር (ስእሉን የፀጉር አሰራር ስር ተመ.)። 2.ጎንና ጎኑ ተላጭቶ ከግንባሩ እስከ ማጅራቱ ድረስ የሚቀር የወንድ ልጅ ፀጉር(ስእሉን የፀጉር አሰራር ስር ተመ.)። 3. ለአካለ መጠን ያልደረሰች ወይም ያልደረሰ ልጅ።

ጋምቤሎ(ገምቤሎ) ስ የዛፍ አይነት።

ጋረ ግ ጣረ፥ ለፋ፥ ደከመ።

ጋረደ ግ 1. ሸፈነ፥ ከለለ። 2. ማየት ከለከለ። *አይኑን ጋረደው።*

መጋረጃ ስ መስኮት፣ በር፣... ላይ የሚዘረጋ ጨርቅ (ለመከለያ ወይም ለጌጥ)።

መጋረጃ ተጣለ መጋረጃ ተጋረደ።

ግርዶሽ(ግርጃ) ስ መከለያ ወይም ከለላ።

ጋረጠ ግ 1. ሂጨረ፥ ቀደደ (መተላለፊያ ላይ ያለ ሹል ነገር፣ እሾክ፥...)። 2. ደነቀረ፥ መተላለፊያ ዘጋ፣ አወከ። 3. ሰካ፥ ተከለ።

ጋሬጣ ስ 1. እንደ እንጨት ስንጣሪ ወይም እሾክ ያለ ነገር። 2. እንቅፋት ወይም መሰናክል።

ተጋረጠ ግ 1. ፊት ለፊት በመቆም ለማየት ወይም ለመሄድ ከለከለ። 2. እንቅፋት ወይም መሰናክል ሆነ። 3. ተሰካ፥ ተተከለ።

ጋሪ ስ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ተሽከርካሪ ጎማዎች ያሉት በፈረስ ወይም በበቅሎ የሚጎተት መጓጓዣ።



ጋሪ

ጋሪ ነጂ ስ ጋሪ የሚነዳ ሰው።

ጋሪያት ስ የቀጣኑነት፥ የብስጩነት፥ የሞገደኝነት፥... ባህርይ።

ጋሪያታም ቅ ቀጣኑ፥ ብስጩ፥ ሞገደኛ፥ እልከኛ።

ጋራ^{1} ስ ተራራ

ጋራማ ቅ ተራራማ።

ጋራ^{2} "ጋር"ን ተመ.

***ጋራ**

የጋራ ቅ ከአንድ በላይ ባለቤት ያለው፣ የግል ያልሆነ፥ የወል። *ሃብቱ የጋራችን ነው /የጋራ ንብረት አለን።*

የጋራ መግለጫ ስ መንግስታት፥ የፖለቲካ

ድርጅቶች፥... በተለያዩ ጉዳዮች ላይ አንድ አቋም በመውሰድ ይፋ የሚያወጡት መግለጫ።

የጋራ ስምምነት ስ ሁሉንም ወገኖች ሊጠቅም በሚችል ጉዳይ ላይ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ወገኖች የሚፈራረሙት ውል።

የጋራ ድንበር ስ የተለያዩ ሃገሮችን የሚያዋስን ቦታ።

ተጋራ ግ ተካፈለ። *የተገኘውን ትርፍ ከወንድሙ ጋር ተጋራ።*

አጋራ ግ አካፈለ።

ጋራማ "ጋራ¹" ስር ተመ.

ጋራዥ ስ የተለያዩ ተሽከርካሪዎች የሚታደሱበት ወይም የሚጠገኑበት ቦታ፥ ድርጅት።

ጋሬ ስ ዘንጋዳ፥ ገብስ፥ ስንዴ፥... በመቀላቀል የሚዘጋጅና ብዙውን ጊዜ ከበኔፍ እንጀራ ስር የሚጎዘጎዝ ወፍራም እንጀራ።

ጋሬጣ "ጋረጠ" ስር ተመ.

ጋር (ጋራ) ከ" ከ-" በመጣመር "አብሮ" የሚለውን ሃሳብ የሚገልፅ ቃል። *ከአበባ ጋር ሄደ ።*

ጋሸበ ከተገቢው በላይ በጣም አድጎ ወይም በዝቶ ተጋደመ፥ ወደቀ(የተዘራ እህል)።

ግሸበት "ዋጋ" ስር "የዋጋ ግሸበት"ን ተመ.

ጋሻ¹ ስ 1. ከጎሽ ወይም ከዝሆን ወይም ከጉማሬ ወይም ከበሬ ቆዳ የሚሰራ፥ ብዙውን ጊዜ ክብ የሆነ ቅርፅ የሚኖረውና ከውስጥ በኩል የእጅ ማስገቢያ ወይም ማንገቻ ያለው፥ በውጊያ ጊዜ ለጦር ወይም ለጎራዴ፥... መመከቻ በእጅ የሚያዝ የጦር እቃ። 2. (ዘይ.) መመኪያ፥ አለኝታ።

ጋሻ 1ኛ ፍቺ

ጋሻ ጃግሬ ስ የጦር መሳሪያ ተሸክሞ ጌታውን የሚከተል አሽከር።

ጋሻ ሰጓጅ ስ ጋሻ የሚሰራ ባለሙያ።

ጋሻ² ስ የመሬት ስፋት መለኪያ(አንድ ጋሻ መሬት አርባ ሄክታር ነው)።

ጋሼ ስ በእድሜ አነስ የሚል ሰው በእድሜ የሚበልጠውን ወንድ የሚጠራበት የአክብሮት ስም።

ጋበን¹ ስ ሩር ወይም ጥንግ።

ጋበን² ስ ወበቅ።

ጋበዘ ግ 1. በማብላት ወይም በማጠጣት አስተናገደ። 2. በአንድ ነገር ላይ እንዲሳተፍ ወይም አንድን ነገር (ቲያትር፥ሲኒማ፥...) እንዲመለከት ወሰደ፥ ጠራ።3. ሳበ፥ ገፋፋ። *ፊቷ ይጋብዛል /ለጠብ የጋበዘኝ እሱ ነው።*

ግብዣ ስ 1. የመብልና የመጠጥ መስተንግዶ። 2. አንድን ነገር እንዲመለከቱ ወይም አንድ ነገር ላይ እንዲሳተፉ የሚቀርብ ጥሪ ወይም ጥያቄ።

የግብዣ ወረቀት ስ የጥሪ ወረቀት።

ተጋበዘ ግ 1. ግብዣ ተጠራ ተደረገለት። 2. ልማታ ወይም ልደባደብ አለ፥ ተገለገለ።

ተጋባዥ ቅ ግብዣ የተደረገለት(እንግዳ)።

ጋቢ ስ በወፍራሙ የተፈተለ ጥንድ ነጠላ በአንድ ላይ ተሰፍቶ የሚዘጋጅና ከላይ የሚለበስ ወፍራም ሸማ።

ጋቤጣ ስ 1. ከኒኬል የሚሰራ ኩባያ የሚመስል የውሃ መጠጫ እቃ። 2. ከኒኬል የሚሰራና ብዙውን ጊዜ ለቅቤና ለወተት መያዣ የሚያገለግል ባለማንጠልጠያ እቃ።

ጋብ

ጋብ አለ ግ በረድ ወይም ቀነስ አለ። *ጫጫታው ጋብ አለ/ዝናቡ ጋብ አለ።*

ጋብቻ "ገባ" ስር ተመ.

ጋተ ግ በግድ ይዞ አጠጣ።

አጋተ ዝ.ከ.

ተጋተ ግ በብዛት ጠጣ።

***ጋተ**

ግት ስ ወተት በብዛት ቋጥሮ ወይም አጠራቅሞ የያዘ የላም፥የፍየል፥ የበግ፥... ጡት።

አጋተ ግ ወተት በብዛት ያዘ(ጡት)።

ጋት ስ የእጅ ጣቶች በመዳፉ ሲቀመጡ ከትንሿ ጣት እስከ ሌባ ጣት ድረስ ያለው ስፋት ወይም የክንድ አንድ ስድስተኛውን ያህል የሚሆን ርዝመት።

ጋኔን(ጋኔል)(ብ.ቁ.አጋንንት) ስ 1. ሰይጣን፥ ርኩስ መንፈስ። ቅ 2. (ዘይ.) ክፉ፥ ርኩስ።

ጋኔን አደረበት ርኩስ መንፈስ ያዘው።

ጋኔን ጎታች ስ በድግምት ጋኔን የሚጠራ አስማተኛ።

ጋኔናም ቅ (ዘይ.) ተናዳጅ፥ ቁጡ።

ጋን ስ 1. ከሸክላ የሚሰራ የጠጅ ወይም የጠላ መጥመቂያ። 2. የ"ውሃ ጋን" ን፥ "ኤሌክትሪክ ጋን"ን ተመ.

ጋን ጋን አለ ግ አፉ ጠላ ጠላ ወይም ጠጅ ጠጅ ሸተተ።

የጋን መብራት ስ እውቀቱንና ችሎታውን

ለሌሎች ያላስተሳሰፈ፥ ያላስተማረ፥ ሌሎች እንዲጠቀሙበት ያላደረገ ሰው።

ጋንድያ ስ 1. ትልቅ፥ ጠረንገሎ። 2. (ስድብ) መኝታ የሚያበዛ ወይም ሰነፍ።

ጋንጃ ስ ማጅራት።

ጋንቢጥ ስ (ስድብ) ያልተቀጣ፥ ባለጌ።

ጋንጩር ስ 1. ጋኔን፥ ሰይጣን። 2. (ስድብ) ሰይጣናም።

***ጋዘ^{1}**

ተጋዘ ግ አንድ እቃ ከቦታ ወደ ቦታ ተወሰደ ወይም ተጓጓዘ።

አጋዘ ግ እቃን ከቦታ ወደቦታ ወሰደ ወይም አጓጓዘ።

***ጋዘ^{2}**

ግዞት ስ አንድን ሰው ከሚኖርበት አካባቢ አንስቶ ወደ ሌላ አካባቢ በመውሰድና በዚያው ቦታ ብቻ ተወስኖ እንዲቆይ የሚደረግበት የእስራት አይነት።

ግዞተኛ ቅ በግዞት ላይ ያለ (ሰው)።

ተጋዘ ግ በግዞት እንዲቀመጥ ተደረገ።

አጋዘ ግ በግዞት አስቀመጠ።

ጋዘና ስ ከቀርከሃ የሚሰራና ለእንጀራ ማስቀመጫ የሚያገለግል እቃ።

ጋዜጣ ስ የተለያዩ ዜናዎች፥ ማስታወቂያዎች፥... በየቀኑ ወይም በየወሩ ወይም በሌላ የተወሰነ ጊዜ ታትመው የሚወጡበት ወረቀት።

ጋዜጠኛ ስ ዜናን ወይም ሌሎች ፕሮግራሞችን ለመገናኛ ብዙሃን የሚያጠናቅር፥ የሚያዘጋጅና መረጃን ለህዝብ የሚያቀርብ ባለሙያ።

ጋዜጣዊ መግለጫ "ፕሬስ ኮንፈረንስ"ን ተመ.

ጋዝ ስ 1. ወደ ፈሳሽነት ወይም ጠጣርነት ለመለወጥ የሚያበቃው የሙቀት ወይም የቅዝቃዜ መጠን ካላገኘ በስተቀር እንደ አየር ሆኖ የሚገኝ ንጥረ ነገር። 2. ለመብራት፥ ለማብሰያ፥... የሚያገለግል ነዳጅ።

ጋዝ ጋዝ አለ ቻከ፥ ተሰለቸ።

ጋገ ስ የሳር አይነት።

ጋየ ግ ነደደ፥ ተቃጠለ።

ጋይ ስ ጥሩ ሰብል ሊይዝ ይችላል በሚል እምነት የእርሻን አፈርና ጓል እየቆለሉ በእሳት የማጋል ወይም የማቃጠል ድርጊት።

አጋየ ግ አነደደ፥ አቃጠለ።

ጋዱ ስ ወንበዴ፥ ቀማኛ።

ጋዲ ስ በቀንድ ከብቶች የኋላ እግር ላይ ከጭን በታች ከጉልበት ማጠፊያ በስተኋላ በኩል የሚገኝና ላም በምትታለብበት ጊዜ ማሰሪያው (የጋዲ ጠፍር) የሚውልበት ቦታ።

ጋዲ [ጠፍር] ስ ላም በምትታለብበት ጊዜ ወዲያና ወዲህ እንዳትል በእግሯ ላይ የሚታሰር ጠፍር።

ጋድ(ገሃድ) ስ በገና ወይም በጥምቀት በአል ዋዜማ የሚውል የፆም ቀን።

ጋድሚያ "*ገደመ" ስር ተመ

ጋድም ዝ.ከ.

ጋገረ ግ የእንጀራን፥ የዳቦን፥... ሊጥ በሰግ ምጣድ ላይ አስፈቶ፥ ጠፍጥፎ በማብሰል እንጀራ፥ ዳቦ፥... አዘጋጀ።

ጋጋሪ(እንጀራ ጋጋሪ) ስ መተዳደሪያዋ እንጀራ ለሌሎች ሰዎች መጋገር የሆነ ሴት።

ጋጋ ግ መታ ወይም አጮለ። *በጥፊ ጋጋው።*

***ጋጋ**

ጋጋታ ስ ትርምስ፥ ግርግር።

ተንጋጋ ግ በብዛት ግር ብሎ ሄደ።

አንጋጋ ግ በብዛት አመጣ ወይም ወሰደ።

ጋጋሪ "ጋገረ" ስር ተመ.

ጋጋታ "*ጋጋ" ስር ተመ.

ጋጋኖ ስ አንገቱ ላይ ሁለት እንጥልጥል ያለው፥ በውሃ አካባቢ የሚገኝ፥ ሲጮህ አስደንጋጭ ድምፅ የሚያሰማና የወንዝ አሞራ የሚመስል የአሞራ አይነት (በእሉን አሞራ ስር ተመ.)።

ጋግርት ስ 1. አይንን የሚያስፈጥጥና ዝም የሚያሰኝ ወይም ንግግር የሚያስጠላ ህመም። 2. ከሰው ተለይቶና ዝም ብሎ ለብቻ የመቀመጥ ባህርይ ወይም ጠባይ።

ጋግርት አለባት ወንድ የሚያስጠላ በሽታ አለባት (ወንድ እንዲጠጋት አትፈልግም)።

ጋግርታም ቅ 1. ጋግርት ያለበት። 2. ከሰው ጋር ተቀላቅሎ መቀመጥ፥ መጫወት፥... የማይወድ። 3. እምቢ ወይም አሻፈረኝ ካለ የማይመለስ፥ በጣም እልሀኛና ንዴተኛ የሆነ።

ጋጠ ግ 1. በጥርሱ እየነጨ፥ እየገሸለጠ ወይም እየላጠ በላ። *ሳር ጋጠ /ለምንት ጋጠ።* 2. አግ፥ *ሰው ሲግጡ ነው የሚውሉት።*

ግጠህ ውጣው ችግርህን እራስህ ታግለህ ተወጣው።

ግጦሽ ስ በሜዳ ላይ የሚገኝና ከብቶች የሚግጡት ሳር።

ተጋጋጠ ግ ብዙ ቦታ ላይ ተላላጠ ወይም ተገሸላለጠ።

አጋጠ ግ ከብቶችን ወደ ግጦሽ አሰማርቶ ሳር እንዲበሉ አደረገ።

ጋጠረ ግ ባረ፥ጋረ፥ለፋ።

ኣጋጠረ ግ 1. ጋጠረ። 2.አለፋ፥ አደከመ።

ጋጠጠ ግ ሟጠጠ፡ ምንም ሳያስቀር ሙልጭ አድርጎና ከስሩ ቆርጦ አነሳ፥ አወደ።

ጋጥ(ጋጣ) ስ የበቅሎ፡ የፈረስ፥ የአህያ ፥... ማደሪያ ቤት።

ጋጠወጥ ቅ (ስድብ) ስነስርአት የሌለው፥ መረን፥ ባለጌ።

ጋፈ ግ 1. አፈሰ፡ ጠረገ። 2. (ዘይ.) በብዛት ጠጣ (ጠጅን፡ ጠላን፡..)።

መጋፊያ ስ 1. ብራኳ። 2. ለአሻሮ ማንኮሪያ የሚሆን የብራኳ አጥንት ወይም በብራኳ አጥንት ቅርፅ ከብረት ወይም ከእንጨት ተሰርቶ ለተመሳሳይ አገልግሎት የሚውል እቃ።

***ጋፈጠ**

ተጋፈጠ ግ 1. ተጋለጠ። 2. በአንድ ጉዳይ፡ ስራ፡... ላይ እውቀቱን፡ ጉልበቱን፥....ሳይቆጥብ ሙሉ በሙሉ ተሳተፈ ወይም ሰራ።

አጋፈጠ ግ አጋለጠ፡ አሳልፎ ሰጠ።

ጋፈፈ ግ በብዛት ሰበሰበ፡ አግበሰበሰ።

አጋፈፈ ዝ.ክ.

ጋፊኛ ስ የተገላቢጦሽ። *እኔ በተበደልኩ ጋፊኛ እሱ አኮረፈኝ።*

ጋፍ ቅ ምኝ፥ ቂል።

ጌ የ"ገ" ፊደል ሃምስ ዘር።

ጌሾ ስ ቅጠሉና እንጨቱ እየተወቀጠ ወይም እየተቀቀለ ለጠላና ለጠጅ መጥመቂያ የሚሆን፡ መረር ያለ ጣእም ያለው የተክል አይነት።

ጌታ ስ 1. ሃብታም፥ ባለፀጋ። 2. አምላክ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ። 3. ባለቤት። *የዚቱ ጌታ ማነው?* 4. አለቃ፥ የበላይ።

ለጌታ አደረ ለሃብታም አሽከር ወይም ሎሌ ሆነ፤ የጌታ አደረም ይባላል።

ጌቶች (በቅርፁ ብ.ቁ. ቢመስልም የሚያገለግለው በነ.ጠቁ. ነው) በአብዛኛው አሽከሮች ወንድ ቀጣሪያቸውን በአክብሮት ለመጥራት የሚጠቀሙበት ቃል።

ጌኛ ስ መጋጋር፡ ለእቃ ማጓጓዣነት የሚያገለግል ፈረስ።

ጌጠኛ "*ገየጠ" ስር ተመ.

ጌጣጌጥ ዝ.ክ.

ጌጥ ዝ.ክ.

ግ የ"ገ" ፊደል ሳድስ ዘር።

ግሁስ ስ ባህታዊ፥ መናኝ።

ግለሂስ "ግል" ስር ተመ.

ግለሰብ ዝ.ክ.

ግለት "ጋለ" ስር ተመ.

ግለኛ "ግል" ስር ተመ.

ግላሎ "*ገለለ" ስር ተመ.

ግላስ ስ ከሃር ወይም ከጎምጃ...የተሰራ የክርቻ ልብስ

ግላዊ "ግል" ስር ተመ.

ግላጭ "ገለጠ" ስር ተመ.

ግል

የግል ቅ 1. የራስ፡ የብቻ። 2. የመንግስት ይዞታ ያልሆነ።

የግል ማህደር ስ በመስሪያ ቤት ውስጥ የአንድን ሰው የህይወት ታሪክ፡ የትምህርት ማስረጃ፡ የስራ አፈፃፀም፡... የያዙ ሰነዶች በአንድ ላይ የሚገኙበት ማህደር፥ ፋይል ።

ግለሂስ ስ ስህተትን ወይም ጥፋትን አምኖ በመቀበል በገዛ ራስ ላይ ሂስ ማካሄድና ራስን በራስ መውቀስ፥ መተቸት።

ግለሂስ አደረገ /አካሄደ እራሱን በራሱ ወቀሰ (በስብሰባ ላይ)።

ግለሰብ ስ አንድ ሰው።

ግለኛ ቅ 1. ብቸኛ። 2. ለራሱ ብቻ የሚያደላ።

ግላዊ ቅ የግል።

ግልሙትና "ገለሞተ" ስር ተመ.

ግልምቢጥ(ግርምቢጥ) የተገላቢጦሽ።

ግልምጫ "ገላመጠ" ስር ተመ.

ግልቢያ "ጋለበ" ስር ተመ.

ግልባጭ "ገለበጠ" ስር ተመ.

ግልብ "ገለበ^{2}" ስር ተመ.

ግልብልብ "*ገለበለበ" ስር ተመ.

ግልብጥ "ገለበጠ" ስር ተመ.

ግልቱ "*ገለታ" ስር ተመ.

ግልዮት ስ በዕፁፍ ዳርና ዳር እንዲሁም በመሃል ከጥራዙ ግራና ቀኝ ያለው ያልተፃፈበት ቦታ።

ግልድም "*ገለደመ" ስር ተመ.

ግልድምሽ ዝ.ክ.

ግልድው

ግልድው አለ ግ ወደቀ፥ ተኛ፥ ተጋደመ።

ግልድው አደረገ ግ ጣለ፡ አጋደመ፡ አስተኛ።

ግልገል ስ የበግ ፥ የፍየል ፡ የድመት፡... ያልጠነከረ ልጅ።

ግልገል ሙሴ ስ የፅዋ ማህበረተኞች ምክትል አለቃ፡ አስተናባሪ።

ግልገል ሙቀጫ ስ ዘነዘና ፤ የሙቀጫ ልጅ።

ግልገል ሚዜ ስ ከዋናው ወይም ከአንደኛው ሚዜ ቀጥሎ ያለ ምክትል ሚዜ።

ግልገል ሞራ ስ ከወተት አንጀት ጋር የሚገኝ ሞራ ወይም ስብ።

ግልገል ሰኮና (ሸኮና) ስ ከሰኮና(ሸኮና) በላይ ያለ የእንስሳት ትንሽ ጥፍር፤ ጉጥ።

ግልገል አንሳ ስ የሉስ፤ ትልቅ አሞራ።

ግልጋሎት "*ገለገለ" ስር ተመ.

ግልግል "ገላገለ" ስር ተመ.

ግልጥ " ገለጠ" ስር "**ግልፅ**" ን ተመ.

ግልፅ "ገለጠ" ስር ተመ.

ግልፋፊ "ገለፈፈ" ስር ተመ.

ግልፍ

ግልፍታ ስ ቁጣ፥ ንዴት፥ ብስጭት፤ በቀላልና በትንሽ ነገር ምክንያት ቶሎ ቱግ ማለት።

ግልፍተኛ ቅ በትንሹ ነገር ቶሎ የሚቆጣ።

ግልፍ አለው ግ ድንገት ተቆጣ።

ግልፍጥ "ገለፈጠ" ስር ተመ.

ግልፍፍ "ገለፈፈ" ስር ተመ.

ግመል ስ ቁመቱና አንገቱ ረዥም፥ በበረሃማ ቦታ የሚኖር፥ ውሃ ጥም ቻይ የሆነና ሻኛ ያለው የቤት እንስሳ(በእሉን የቤት እንስሳ ስር ተመ.)፤

የግመል ሽንት (ዘይ.) በቃሉ የማይረጋ፥ ተንሸራታች።

ግመሬ "ገመረ" ስር "**ገመሬ**"ን ተመ.

ግሙት "ጋመ" ስር ተመ.

ግማሽ "ገመሰ" ስር ተመ.

ግማታም "ገማ" ስር ተመ.

ግማት ዝ.ከ.

ግም ዝ.ከ.

ግ̇ም̇

ግ̇ም̇ አለ ግ 1. ጀመረ፥ ገባ(ክረምት)። *ሃምሌ ግም ሲል።* 2. እንደ መድፍ ያለ መሳሪያ ሲተኮስ የሚያሰማውን አይነት ድምፅ አሰማ።

ግምል "ገመለ" ስር ተመ.

ግምበኛ "ገነባ" ስር "**ግንበኛ**"ን ተመ.

ግምባር "**ግንባር**"ን ተመ.

ግምባታ "ገነባ" ስር "**ግንባታ**"ን ተመ.

ግምብ "ገነባ ስር" "**ግንብ**"ን ተመ.

ግምት "ገመተ" ስር ተመ.

ግምጃ ስ ቀይ ሱቲ።

ግምጃ ቤት ስ 1. የመስሪያ ቤት፡ የድርጅት፤... ንብረት ወይም ገንዘብ ማስቀመጫ ቤት። 2. የግምጃ ቤት ሃላፊ።

ግምገማ "ገመገመ" ስር ተመ.

ግሬን ስ ላም ስትወልድ መጀመሪያ የሚታለበው ቀይ መሳይ የሆነ ወፍራም ወተት፤ እንገር።

ግሩም "ገረመ^{2}" ስር ተመ.

ግሪሳ ስ ብዙ ሆኖ የሚሄድና በማሳ ላይ ያለን እህል በመብላት ከፍተኛ ጥፋት የሚያደርስ የወፍ አይነት።

ግራ ስ 1. የቀኝ ተቃራኒ (አንድ ሰው ፊቱን ወደ ፀሃይ መውጫ ሲያደርግ በስተሰሜን በኩል የሚገኘው የሰውነት ክፍል ወይም ቦታ። 2. ቀና ያልሆነ፡ ጠማማ።

ግራ ገባው 1. ተደናገረ፡ ግር አለው። 2. ተጨነቀ።

ግራ አጋባ አደናገረ፤ አወከ።

የግራ ዳኛ ስ በችሎት ላይ ሆነው ፍርድ በሚሰጡበት ጊዜ ከመሃል ዳኛው በስተግራ በኩል የሚቀመጥ ዳኛ።

ግራ ቀኝ ተመለከተ 1.በሁለት ተቃራኒ ወገኖች ወይም ባለ ጉዳዮች መካከል ሆኖ ሁለቱም የሚሉትን አዳመጠ ወይም ተመለከተ (ውሳኔ፡ ፍርድ፤...ለመስጠት)። 2. ረጋ ብሎ ወደ ቀኝም ወደ ግራም ልብ አድርጎ አየ ወይም አስተዋለ።

ግራ አዝማች ቅ በግራ በኩል ያለውን ጦር ለሚያዘምት የጦር አለቃ ይሰጥ የነበረ ማእረግ።

ግራ እጅ ስ በስተግራ በኩል የሚገኘው የሰው አንደኛው እጅ።

ግራ ክንፍ ስ ሶሻሊስታዊ ወይም ኮሚኒስታዊ አመለካከት ያለው የፖለቲካ ጎራ፥ ቡድን፥...።

ግራ ወንበር ስ የግራ ዳኛ።

ግራ ጌታ ስ (ቤ.ክህ.) በቅኔ ማህሌት ላይ የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ(አለቃ) ከሚቆምበት በስተግራ በኩል የሚቆም፡ ማእረጉ ከቀኝ ጌታው ዝቅ ያለ የመዘምራን አለቃ።

ግራኝ ቅ በግራ እጁ የሚበላ፡የሚሰራ፥...።

ግራማፎን ስ የሸክላ ማጫወቻ መሳሪያ።

ግራም ስ የክብደት መለኪያ (1/1000 ኪሎ ግራም የሚመዝን)።

ግራምጣ ስ በቆላና በወይናደጋ በረግረግ ውስጥ የሚበቅልና ለስፌት ስራ የሚያገለግል፥ ግንዱ አራት ማእዘንነት ያለውና እንደ ቂጠማ ወፍራም የሆነ የሳር አይነት።

ግራር ስ እሾህ ያለው፤ ልቡ ጠንካራ የሆነና በብዛት በሞቃት አካባቢ የሚበቅል የዛፍ አይነት።

ግራሶ ስ ብሎኖች፥ የብረት ጥርሶች፥... እንዳይዝጉና እንዳይጣበቁ ለማለስለሻነት የሚያገለግል ወፍራም ቅባት።

ግራት "ገራ^{1}" ስር ተመ.

ግራኝ "ግራ" ስር ተመ.

ግራዋ ስ ቅጠሉ እንደ ጋን፥ እንስራ ላሉ የጠላ መጥመቂያ እቃዎች በማጠቢያነት የሚያገለግል መራራነት ያለው የእፅዋት አይነት።

ግራዋ ግራዋ አለ ጣእሙ መረረ።

ግራጫ ቅ በነጭና በጥቁር መካከል ያለ አመድማ የቀለም አይነት።

ግራፍ ስ የአንድን ነገር መጠን፥ እድገት፥... የመሳሰሉትን ለማሳየት በወረቀት ላይ የሚሳሉ፥ ቀጥታ ወይም ቀጥታ ያልሆኑና አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ መስመራዊ ምልክቶች።



ግራፍ

ግሬራ ስ ለወተት ማለቢያ የሚያገለግል ከስፌት ወይም ከቅል የሚዘጋጅ ሙሮ ወይም እኮሊ።

ግር "ገራ^{1}" ስር ተመ

ግር

ግር አለ ግ ተደናገረ፥ ተምታታ።

ግርማ ስ 1. ሞገስ፥ ክብር። 2. ግርማ ሞገስ። *ሲያዩት ግርማው ያስፈራል።*

ግርማ ሞገስ ስ በተፈጥሮ የሚታደሉት የመፈራትና የመከበር ፀጋ።

ግርማዊ (አን. ሴት **ግርማዊት**) ቅ የንጉስ የአክብሮት መጠሪያ ።

ግርምቡድ(ግርንቡድ) ስ 1. ለመቀመጫነት የሚያገለግል የግንድ ጉራጅ 2. በርጩማ።

ግርምቢጥ (ግርንቢጥ) "**ግልምቢጥ**"ን ተመ.

ግርሻ "ገረሸ" ስር ተመ.

ግርንቡድ "**ግርምቡድ**"ን ተመ.

ግርንቢጥ "**ግርምቢጥ**"ን ተመ.

ግርንድስ (ስድብ) እንቅልፍ የሚያበዛ ወይም ተኃድሞ የሚውል።

ግርንግሬት ስ ሁለት እጅን ወደሃላ በማድረግ የሚታሰር የእስር አይነት ፤ ፊጥኝ።

የግርንግሬት ታሰረ የፊጥኝ ታሰረ።

ግርዘት "ገረዘ" ስር ተመ.

ግርዝ ዝ.ክ.

ግርድ ስ አውድማ ላይ ምርቱ(ፍሬው) ከገለባ በሚለይበት ጊዜ ከዋናው ምርት ውስጥ እየተንገዋለለ የሚወገድ የእህል ፍሬ ስብርባሪ፥ በደንብ ፍሬ ያልያዘና በእንቡጥነት የቀረ እንጭጭ፥ ብጣሪ፥ ንፋሽ፥... ያለበትና ደረጃው ዝቅተኛ የሆነ የምርት ክፍል።

ግርድና "ገረደ" ስር ተመ.

ግርድፍ "ገረደፈ" ስር ተመ.

ግርዶሽ "ጋረደ" ስር ተመ.

ግርጃ "ጋረደ" ስር "**ግርዶሽ**"ን ተመ

ግርጊ ስ 1. በመኝታ ጊዜ እግር የሚውልበት ቦታ። 2. ቢታች፥ ስር። *ቤቱ ከተራራው ግርጌ ነው።*

ግርግም ስ ከድንጋይ ወይም ከእንጨት የሚሰራ የከብቶች መኖ መብለያ ወይም መመገቢያ።

ግርግራ^{1} (ጊርጊራ) ስ ከሸክላ ወይም ከቆርቆሮ፥... የሚሰራ የእጣን ማጨሻ እቃ (ስእሉን የሸክላ እቃ ስር ተመ.)።

ግርግራ^{2} ስ ሲታረስ የሚያስቸግር ጭንጫ መሬት።

ግርግራት ስ ሴቶች እንደ ብርጉድ የመሳሰሉ ጥሩ መአዛ ያላቸውን የእፅዋት ጢስ የሚታጠኑበት፥ እንደ ሰዋ ያለ እግር ያለው የሸክላ እቃ።

ግርፊያ "ገረፈ" ስር ተመ.

ግርፉት ዝ.ክ.

ግርፍ ዝ.ክ.

ግሮሰሪ ስ 1. መጠጥ በጅምላም ሆነ በመለኪያ የሚሸጥበት የንግድ ቤት።2. ልዩ ልዩ የምግብ ሸቀጣሸቀጦች የሚሸጡበት የንግድ ቤት።

ግሳታም "*ግሳ" ስር ተመ.

ግሳት ዝ.ክ.

ግሳንግስ ስ 1. ዝባዝንኬ፥ ግብስብስ። 2. ኮተት።

ግሳንግሳም ቅ 1. እሰሩን ገሰሩን ሁሉ የሚሰበስብ። 2. ኮተታም።

ግሳፄ(ግሳጤ) "ገሰፀ" ስር ተመ.

ግስ "ገሰሰ^{3}" ስር ተመ.

ግስላ ስ 1. ቁጡ የሆነ ነብር መሳይ አውሬ። ቅ 2. ሃይለኛ፥ ቁጡ።

ግሽልጥ "ገሸለጠ" ስር ተመ.

ግሽርጥ "ጉሽርጥ" ን ተመ.

ግሽበት "ጋሸበ" ስር ተመ.

ግሸጣ ስ ቅርፁ ልብ የሚመስል የሚበላ ፍሬ የሚያፈራና በቆላ አካባቢ የሚበቅል፥ ፍሬውና ስሩ ለመድሃኒትነት ያገለግላል የሚባል የእፅዋት አይነት፤ ፍሬውም ግሸጣ ይባላል።

ግብቡ "ገባ" ስር ተመ.

ግቢ ዝ.ከ.

ግብ ዝ.ከ.

ግብረ ሃዋርያ "*ገበረ¹" ስር ተመ.

ግብረ ሰዶም ዝ.ከ.

ግብረ ስጋ ዝ.ከ.

ግብረ አበር ዝ.ከ.

ግብረ ገብ ዝ.ከ.

ግብረ በላ "ገበረ" ስር ተመ.

ግብረ ጠል ዝ.ከ.

ግብር¹ "ገበረ" ስር ተመ.

ግብር² "*ገበረ¹" ስር ተመ.

ግብርና "*ገበረ²" ስር ተመ.

ግብር ውሃ ሰ ሴቶች ማታ ከመኝታ በፊትና ጠዋት ስራ ከመጀመራቸው በፊት ብልታቸውን የሚታጠቡበት ውሃ።

ግብር ውሃ ወጣች ማታ ከመኝታ በፊት ወይም ጠዋት ከስራ በፊት ብልቷን ታጠበች።

ግብስብስ "*ገበሰበሰ" ስር ተመ.

ግብአተመሬት"ገባ" ስር "ግባተመሬት"ን ተመ.

ግብዝ "*ገበዘ" ስር ተመ.

ግብዣ "*ጋበዘ" ስር ተመ.

ግብይት "ገበየ" ስር ተመ.

ግብዳ "ገበደ" ስር ተመ.

ግብግብ ሰ ትግል ወይም ትንቅንቅ።

ግብጣ ሰ ልብስ ሲጠብ ወሽመጥ ሆኖ የሚገባ ቁራጭ ጨርቅ።

ግብጦ ሰ በአብዛኛው በጎጃም አካባቢ የሚበቅልና ባቄላ መሳይ ሆኖ መራራ ጣእም ያለው የአበባ እህል።

ግተት "ገተተ" ስር ተመ.

ግት "*ጋተ" ስር ተመ.

ግትልትላም "*ገተለተለ" ስር ተመ.

ግትልትል ዝ.ከ.

ግትር "ገተረ" ስር ተመ.

ግትት "ገተተ" ስር ተመ.

ግትቻ ዝ.ከ.

ግነት "ገነነ" ስር ተመ.

ግን ቀደም ብሎ በተነገረው ነገር ላይ አፍራሽ ወይም አጠራጣሪ የሆነ ሃሳብ ወይም እረፍተ ነገር ለማስከተል ሲፈለግ የሚገባ ማያያዣ። መደበኛ በሆነ ሁኔታ ላይ ብዙ ጊዜ "ነገር ግን" ይባላል። *መጻፉን ወሰድኩ፤ ግን ቶሎ እንድትመልስ /ቶሎ እጠብቅሃለሁ፤ ግን ካልመጣህ/ ብዙ መሰናክል ገጥሞን ነበር፤ ግን ውጤቱ የተሳካ ሆነ።*

ግንበኛ "ገነባ" ስር ተመ.

ግንባር(ግምባር) ሰ 1. ፀጉር ከበቀለበት የራስ ክፍል በታች ከአይን በላይ ያለ የሰውነት ክፍል(ስእሉን ራስ ስር ተመ.)። 2. ፊት ለፊት። *ቤቱ ግንባር ላይ ነው ያለው።* 3.(ዘይ.) እድል+ ገድ። *ጥሩ ግንባር አለው።* 4. አንድነት+ ህብረት። *ግንባር ፈጥረው ለጠቁት።* 5.ጦርነት የሚካሄድበት መስመር፣ጦር ግንባር። 6. ለጋራ አላማ በአንድ አመራር ስር በመጠቃለል የሚታገሉ የተለያዩ ሃይሎች የሚሰባሰቡበት የፖለቲካ መድረክ ወይም ድርጅት። *ነፃ አውጭ ግንባር።*

ግንባሩ አይታጠፍም ወደኋላ አይልም፣ አይበገርም።

ግንባሩን አስመታ/አስወጋ 1. ወደአንድ ቦታ ለትንሽ ጊዜ ብቅ በማለት መኖሩን አሳወቀ ወይም አሳየ። 2. ደጅ ጠና።

ግንባሩን ከሰከሰ ተኮሳተረ።

የግንባር ስጋ ቅ የማይፈራ፣ እውነቱን ፊት ለፊት የሚናገር።

ግንባረ ቦቃ ቅ ግንባሩ ላይ ነጭ ምልክት ያለበት (ከብት)።

ግንባር ለግንባር ሰ ፊት ለፊት።

ግንባር ቀደም ሰ የመጀመሪያ፣ ቀዳሚ።

ግንባታ "ገነባ" ስር ተመ.

ግንብ ዝ.ከ.

ግንብጥ "*ገነበጠ" ስር ተመ.

ግንቦት ሰ ከሚያዝያ ቀጥሎ የሚመጣ የአመቱ ዘጠነኛ ወር ስም።

ግንቦቴ ሰ በግንቦት ወር የሚዘራ ጉብስ።

ግንትር "ገነተረ" ስር ተመ.

ግንኙነት "*ገነኘ" ስር ተመ.

ግንዘት "ገነዘ" ስር ተመ.

ግንዛቤ"*ገነዘበ" ስር ተመ.

ግንዝ "ገነዘ" ስር ተመ.

ግንድ ሰ 1. በስር አማካኝነት ከመሬት ውስጥ የሚስበውን ውሃና ንጥረ ነገር ተቀብሎ ወደ ተክሉ ቅርንጫፎች አስተላልፎና ቅርንጫፎቹን ተሸካሚ የተክል ትልቁና ወፍራሙ ክፍል (የዛፍን ስእል ተመ.)። 2. ተቆርጦም ሆነ ሳይቆረጥ የሚገኝ ወፍራም እንጨት። 3. የትውልድ ሃረግ መነሻ።

ግንድ የሚያክል ትልቅ ወይም ግዙፍ የሆነ።

ግንደ ቆርቋር ስ በምንቃሩ ግንድ እየቦረቦረ በተቦረቦረው ቦታ ውስጥ የሚኖር ወፍ (ስእሉን ወፍ ስር ተመ.)።

ግንዲላ ስ ሳይፈለጥ ወይም ሳይሰነጠቅ ድፍኑን በተወሰነ ርዝመት የተቆራረጠ ግንድ።

ግንድስ "ገነደሰ" ስር "ግንዳሳ" ን ተመ.

ግንገና "ገነገነ" ስር ተመ.

ግንጣይ "ገነጠለ" ስር ተመ.

ግንጥል ዝ.ከ.

ግንጭል ስ መንገጭላ።

ግንፍልፍል "*ገፈለፈለ" ስር ተመ.

ግኝት "*ገኘኘ" ስር ተመ.

ግኡዝ ስ 1. ተንቀሳቃሽ ያልሆነና ሀይወት የሌለው ነገር። 2. (ዘይ.) የማይናገር(ሰው)።

ግኡዝ ዖታ ስ (ሰዋ.) በተንታዊ የቋንቋ ሊቃውንት ትንተና መሰረት በአንስታይ ወይም በተባእታይ የዖታ መደብ የማይጠቃለል የዖታ አይነት (ለምሳሌ ድንጋይ)።

ግእዝ ስ 1. የጥንት የኢትዮጵያ የስነ ፅሁፍ ቋንቋ የነበረና አሁን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ውስጥ ብቻ በአገልግሎት ላይ የሚገኝ ቋንቋ። 2. ፊደል ገበታ ላይ ቀልቁል የመጀመሪያውን ረድፍ ይዘው የሚገኙት እንደ ሀ፣ለ፣... ያሉት ፊደላት ከዘሮቻቸው ማለትም ከካእብ (ሁ፥ሉ፥...)፥ ከሳልስ (ሂ፥ሊ፥..) ተለይተው የሚታወቁበትና የሚጠሩበት የቅርፃቸውና የረድፋቸው አጠቃላይ መጠሪያ። 3. ከሰሰቱ ያሬዳዊ የዜማ አይነቶች ያንደኛው መጠሪያ።

ግው¹

ግው(እግው) አለ ግ ትልቅ ወይም ወፍራም ነገር ሲጋጭ፥ ሲወድቅ ወይም ሲመታ የሚፈጥረውን አይነት ድምፅ አሰማ።

ግው²

ግው አለ ግ በሃይል ነደደ። *እሳቱ ግው ብሎ ነደደ።*

ግዙፍ "ገዘፈ" ስር ተመ.

ግዛት "ገዛ" ስር ተመ.

ግዝረት "ገረዘ" ስር "ግርዘት"ን ተመ.

ግዝት "ገዘተ" ስር ተመ.

ግዝፈት "ገዘፈ" ስር ተመ.

ግዞተኛ "*ጋዘ²" ስር ተመ.

ግዞት ዝ.ከ.

ግዢ "ገዛ" ስር ተመ.

ግዱፍ "ገደፈ¹" ስር ተመ.

ግዳይ "ገደለ" ስር ተመ.

ግዳጅ¹ "ገደደ²" ስር ተመ.

ግዳጅ² ስ የወር አበባ፥ አደፍ።

ግዴታ "ገደደ²" ስር ተመ.

ግድ ዝ.ከ.

ግድም "ገደመ"ስር ተመ.

ግድርድር "*ገደረደረ" ስር ተመ.

ግድብ "ገደበ" ስር ተመ.

ግድንግዲ (ግድግዲ) ስ የአሞራ አይነት።

ግድንግድ ቅ ወፍራምና ግዙፍ የሆነ።

ግድያ "ገደለ" ስር ተመ.

ግድግዳ "ገደገደ" ስር ተመ.

ግድግዲ "ግድንግዲ"ን ተመ.

ግድፈት "ገደፈ" ስር ተመ.

ግግ ስ ከድድ ውስጥ ወደ ላይ ገና እየበቀለ ያለ የህፃን ጥርስ።

ግግር "ገገረ" ስር ተመ.

ግጥሚያ "ገጠመ" ስር ተመ.

ግጥም ዝ.ከ.

ግጥብ "ገጠበ" ስር ተመ

ግጦሽ "ጋጠ" ስር ተመ.

ግጫ "እንግጫ"ን ተመ.

ግጭት "ገጨ" ስር ተመ.

ግፈኛ "ገፋ" ስር ተመ.

ግፊት ዝ.ከ.

ግፊያ ዝ.ከ.

ግፍ ዝ.ከ.

ግፍልፍል "*ገፈለፈለ" ስር"ግንፍልፍል"ን ተመ.

ግፍጥጥ "ገፈጠጠ" ስር ተመ.

ጎ የ"ገ" ፊደል ሳብእ ዘር።

ጎህ ስ በደንብ ከመንጋቱ በፊት የሚታይ ብርሃን ወይም ውጋጋን።

ጎህ ሲቀድ በደንብ ከመንጋቱ በፊት ባለው ጊዜ።

ጎህ ቀደደ ጨለማው ተገፈፈ፥ መንጋት ጀመረ፥ የፀሃይ ውጋጋን ታየ።

ጎለመ ግ ለየ፥ ከፈለ፥ ለብቻ አደረገ(የእርሻ መሬትን)።

ጉልማ ስ አባት ለልጁ የሚሰጠው ትንሽ የእርሻ መሬት።

ጎለመሰ ግ 1. ጎልማሳ ሆነ። 2. (ዘይ.) አደገ፥ በሰለ (በአእምሮ፥ በአስተሳሰብ)።

ጉልምስና ስ ከወጣትነት በኋላ፥ ከሽምግልና በፊት ያለው የእድሜ ክልል።

ጎልማሳ ስ ከወጣትነት በኋላና ከሽምግልና በፊት ባለው የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ ወንድ (ሰው)።

አጎላማሽ ቅ አጠናካሪ፥ ተጨማሪ (ፊደል፥ ቃል፥...)።

ጎለሰሰ ግ በቀላሉ ጣለ ወይም አጋደመ።

ጉልሽ ቅ አቅመቢስ፥ በቀላሉ የሚወድቅ፥ የሚጋደም።

ጎለበተ ግ ጠነከረ፥ ሃይል አገኘ፥ በረታ።

ጉልበት ስ 1. የጭንና የቅልጥም መጋጠሚያ የሆነና ወደ ውጪ ወጣ ብሎ የሚታይ የሰውነት ክፍል (ስእሉን ሰውነት ስር ተመ.)። 2.አቅም ሃይል፥ ብርታት። 3.(ዘይ.) በስራ ላይ የፈሰሰ ወይም የዋለ ሃይል። *ጉልበቱን በዘበዙት።*

በጉልበት በግድ፥ በሃይል በማስገደድ። *ሴቲቱን በጉልበት አጠቃት።*

በጉልበቱ ያረገዘ ሰነፍ፥ ጉልበት እያለው የማይሰራ።

ጉልበቱን ቆጠበ መስራት የሚችለውን ያህል ከመስራት ተቆጠበ፥ ሰነፈ።

ጉልበቱን አሳየ 1.ሃይሉን፥አቅሙን፥ችሎታውን ተጠቅሞ አሸነፈ፥ ድል አደረገ። 2. የሃይል እርምጃ ወሰደ።

ጉልበቱን አፈሰሰ በስራ ለፋ፥ ደከመ።

ጉልበት ሳመ 1. ጉልበት በመሳም አከበረ፥ አክብሮቱን አሳየ። 2.ተሸነፈ፥የበታችነቱን ተቀበለ።

ጉልበት አወጣ ሃይል አገኘ፥ በረታ።

የጉልበት ስራ ስ የአእምሮ ስራ ያልሆነ(እንደ ሸክም፥ ቁፋሮ፥... ያለ ስራ)።

የጉልበት ሰራተኛ ስ መሸከም፥ መቆፈር፥... በመሳሰሉና ከስልጠና ይልቅ ጉልበትን በሚጠይቁ ስራዎች ላይ የተሰማራ ሰራተኛ።

የጉልበት ዋጋ ስ አንድ ሰው ለሰራው የጉልበት ስራ የሚከፈል ገንዘብ፥ ደመወዝ ወይም ሌላ ነገር።

ጉልበተኛ ቅ 1. ሃይል፥ አቅም ያለው። 2. የፈለገውን በግድ ማድረግ ወይም ማስደረግ የሚችል፥ አመፀኛ።

ጉልበታም ቅ ሃይል ወይም አቅም ያለው።

ጎለተ ግ 1. ጉልቻን ተከለ ወይም አስቀመጠ። 2.በቂጡ አስቀመጠ፥ ቁጭ አደረገ። 3. ያለምንም ስራ ወይም ጥቅም ለረዥም ጊዜ አንድ ቦታ ላይ አስቀመጠ።

ጉልት 1. ስ (ስድብ) ሰነፍ፥ ከተቀመጠበት ተንቀሳቅሶ መስራት የማይወድ። 2. ስ በመንደር ውስጥ፥ በመንገድ ዳር፥... የተለያዩ ሸቀጦች(እንደ ሽንኩርት፥ ድንች፥...የመሳሰሉት) ለዚሁ ስራ ተብሎ በተዘጋጀ መደብ ላይ ተዘርግተው የሚሸጡበት አነስተኛ ገበያ፥ ጉሊትም ይባላል።

ጉልቻ ስ የድስት፥ የምጣድ...ማጣጃ ሆኖ የሚያገለግል ሶስት ድንጋይ ወይም ሸክላ ወይም ከላይ ክብ ሆኖ ሶስት እግሮች እንዲኖሩት ተደርጎ ከብረት የሚሰራ ማጣጃ።

ጉልቻ ራስ ስ (ስድብ) ትልቅ ራስ።

ተጎለተ ግ ያለ ምንም ስራ ወይም ጥቅም ለረዥም ጊዜ አንድ ቦታ ላይ ተቀመጠ።

ጎለንታ(ጉለንታ) ስ ከእርሻ ላይ አፈሩ በጎርፍ እንዳይሸረሸር አፈሩን ዳርና ዳር በመቆለል የሚሰራ የጎርፍ መከላከያ።

ጎለደመ ግ አፈነገጠ፥ከመደበኛ ቦታው ወጣ ብሎ ታየ(አጥንት፥ እንጨት፥...)።

ጉልድም ቅ ያፈነገጠ፥ ወጣ ብሎ የሚታይ(አጥንት፥ እንጨት፥...)።

አጎለደመ ግ ጎለደመ።

ጎለደፈ ግ ደነዘ፥ ዶለዶመ (ለምሳሌ ስለት)።

ጎልዳፋ ቅ 1. ስለት የሌለው፥ ዱልዱም (ቢላዋ፥ምሳር፥...)።2. (ዘይ.) አብራርቶ ወይም አፍታቶ መናገር የማይችል። *አንደበተ ጎልዳፋ።*

ተጎላደፈ ግ አብራርቶ ወይም አፍታቶ መናገር አቃተው።

ጎለጎለ ግ በዶማ ወይም በማረሻ የተነቀለን አረም አፈሩን በማራገፍ ጣለ። 2. ውሉን አጠፋ፥ ተበተበ (የልቃቂትን፥ የክርን፥...)። 3. በጣም ወደ ውጪ አወጣ (ለምሳሌ ምላሱን)። 4. አወጣ፥ ዘከዘከ (ምስጢርን፥ በድብቅ የተፈፀመን ነገር)።

ጉልጓሎ(ጉልጎላ) ስ በዶማ ወይም በማረሻ በተነቀለ አረም ቂጥ ላይ ያለን አፈር የማራገፍና አረሙን ከእርሻው ላይ የማስወገድ ስራ።

ተጎለጎለ ግ 1. አፈሩ እየተራገፈ አረሙ ከእርሻው ላይ ተነሳ፥ ተወገደ።2. ውሉ ጠፋ ተተበተበ(ክር፥ልቃቂት፥...)።3. ወጣ፥ ፈጠጠ (አይን፥ ምላስ፥...)።

***ጎለፈፈ**

ጎልፋፋ ቅ አቅመቢስ፥ በቀላሉ ጉልስስ የሚል።

ጎላ^{1} ግ 1.ጉልህ ሆነ፥ ደመቀ(ፅሁፈት)። 2. ትልቅ

ወይም ግዙፍ ሆኖ ታየ።

ማጉሊያ ቅ አጉልቶ የሚያሳይ ወይም የሚያሰማ መሳሪያ።

ጉልህ ቅ 1. ግልፅ፥ ትልቅ ሆኖ ወይም ደምቆ የሚታይ(ሰሁፍ)። 2. በደንብ የሚታይ፥ የሚታወቅ፥ ከፍተኛ፥ ከባድ። (ለምሳሌ ጉልህ ስህተት፥ አስተዋፅኦ፥...)።

አጎላ ግ 1. ግልፅ፥ ትልቅ ሆኖ እንዲታይ አደረገ። 2. ከፍ ብሎ፥ በደንብ እንዲሰማ አደረገ።

ጎላ² ስ ለንፍሮ፥ ለስጋ፥... መቀቀያ የሚያገለግል በጣም ትልቅ ብረት ድስት ወይም ጉርድ በርሜል።

ጎል ስ ግብ።

ጎል ጠባቂ ስ ግብ ጠባቂ፥ በረኛ

ጎልማሳ "ጎለመሰ" ስር ተመ.

ጎልዳፋ "ጎለደፈ" ስር ተመ.

ጎልፍ ስ አነስተኛና ጠንካራ የሆኑ ኳሶችን ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀ ልዩ በትር በመምታት ብዙውን ጊዜ ቁጥራቸው 9 ወይም 18 በሆኑና ተቆፍረው በተዘጋጁ የመሬት ቀዳዳዎች (ጉድጓዶች) ውስጥ ለማስገባት የሚደረግ ስፖርታዊ ጨዋታ።

***ጎመለለ**

ጎምላላ ቅ ሲሄድ ወይም ሲራመድ የሚጀነን።

ጎምለል ጎምለል አለ ግ ተጎማለለ።

ተጎማለለ ግ በመጀነን ወይም በኩራት ተራመደ፥ ሄደ።

ጎመረ ግ አኮራ፥ በኩራት ወይም በትእቢት ከፈሰ፥ ወጠረ።

ተጎመረ ግ ኮራ፥በኩራት ወይም በትእቢት ተኮፈሰ፥ ተወጠረ።

ጎመራ ግ በሰለ፥ደረሰ(ሰብል፥ፍራፍሬ፥...)።

ጎመተ ግ ሙዳ ሙዳ እያደረገ ቆረጠ ወይም ከፈለ (ስጋን)።

ጎማች ቅ ስጋ ቆራጭ፥ ስጋን በብልትና በሙዳ እየመጠነ የሚቆርጥ።

ተጎመተ ግ በተወሰነ መጠን ተቆረጠ (ስጋ)።

ተኋመተ ግ ተከፈለ (ስጋን)።

ጎመን ስ 1. የተለያየ ዝርያ ያለውና ተቀቅሎ የሚበላ የተክል አይነት (ለምሳሌ የአበሻ ጎመን፥ የጉራጌ ጎመን፥ ጥቅል ጎመን)።

ጎመን በጤና ጭቅጭቅና ውጥረት ካለበት የድሎት ኑሮ ይልቅ ሰላም ያለበት የድህነት ኑሮ ይሻላል ለማለት የሚነገር አባባል።

የጎመን ትል ስ በጎመን ቅጠል ላይ የሚገኝ ቅጠሉን እየተመገበ የሚኖርና መልኩ ቅጠል የሚመስል ትል።

ጎመን ዘር ስ ተወቅጦ ለምግድ ማስሻ እንዲሁም ተጨምቆ የምግብ ዘይት የሚሆን የአበሻ ጎመን ፍሬ።

ጎመዘዘ ግ ሆመጠጠ።

ጎምዛዛ ቅ ሆምጣጣ።

ጎመደ ግ 1. ቆረጠ፥ጎረደ። 2. ገመጠ፥ በላ (ዳቦን፥ ስጋን፥...)። 3. መታ (በዱላ)።

ጉማጅ ቅ ከሳዩ ላይ ተቆርጦለት የቀረው ክፍል ወይም ቁራጭ(ለምሳሌ የእንጨት ጉማጅ ፥ዳቦ ጉማጅ)።

ጉምድ ቅ ቁራጭ።

ጉምድ አለ ግ ማለት ከሚገባው ጊዜ በፊት አለቀ። *ለአንድ ወር የታገዘው ጤፍ በሁለት ሳምንት ውስጥ ጉምድ አለ።*

ጎመድ ስ ቆመጥ፥ ወፍራም ዱላ።

ጎማዳ ቅ 1. ጎራዳ፥ቆራጣ። 2. (ዘይ.) ቶንጋ፥ መልከ ጥፉ። 3. (ስድብ) ውሽታም።

ጎመጀ(ጎመዠ) ግ ተመኘ፥ቋመጠ፥ ጓጓ።

አስጎመጀ ግ አጓጓ ወይም አማረ።

ጎመጎመ ግ 1.መብቀል ወይም መውጣት ጀመረ፥ ጎነቆለ። 2. አጎጠጎጠ፥ መውጣት ወይም ማደግ ጀመረ(ጡት)።

አጎመጎመ ዝ.ክ.

***ጎመጎመ**

ጉምጉምታ ስ 1. ይፋ ያልሆነ፥ ውስጥ ውስጡን የሚወራ ሃሜት፥ቅሬታ፥...። 2. በአንድ ቦታ ላይ የተሰበሰቡ ሰዎች ድምፃቸውን በደንብ ሳያሰሙ በሹክሹክታ ሲያወሩ የሚሰማው የሚያስገመግም ድምፅ።

ጉም ጉም አለ ግ ሃሜትን፥ ቅሬታን፥... በሹክሹክታ ወይም በድብቅ አወራ።

ጎመጫ¹ ስ 1. አገዳው ቀጭን የሆነና ብዙ ዛላ ያለው የሳር አይነት።

ጎመጫ² ስ ማር የለሽ የንብ እንጀራ፥የማር ከፋ።

ጎሚስታ ስ የመኪና ጎማ በመቀየር፥ የተነፈሰ አየር በመሙላት፥ የተቀደደውን በመጣፍ፥... አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት።



ጎማ ስ 1. ከጎማ ዛፍ ከሚገኝ ፈሳሽ በፋብሪካ ውስጥ ከብ ሆኖ ተሰርቶ የሚወጣና ከተሽከርካሪዎች ቸርኬ ላይ እየተገጠመ ተሽከርካሪዎችን ለመሽከርከር የሚያስችላቸው አካል። 2. ጠንካራና ወፍራም ላስቲክ። 3. (ዘይ.) የማይታኘክ፥ ጎማ፥ጭፍጭ እኛ (ስጋ)።

የጎማ ዛፍ ስ እንደመኪና ጎማ፣ የውሃ ጎማ፣ ላስቲክ፣... የመሳሰሉትን ለመስራት የሚያስችል ወተት የመሰለ ፈሳሽ የሚያመነጭ የተክል አይነት።

ጎማ ጫማ ስ ካንላንስ ጎማ እየተቆረጠ የሚዘጋጅ ሽፍን ያልሆነ ጫማ።

ጎማች "ጎመተ" ስር ተመ.

ጎማዳ "ጎመደ" ስር ተመ.

ጎምላላ"ጎመለለ" ስር ተመ.

ጎምቱ ትልቅ ወይም ጨዋ ሰው፣ አዛውንት።

ጎምበሬ(ገንቦሬ) ስ በክረምት ዝናብ ሲዘንብበት ጭቃ የማይሆን የአፈር አይነት።

***ጎረመረመ**

ጉርምርምታ ስ 1. የነጎድጓድ ድምፅ። 2. ተከታታይነት ያለው የመንጓጓት ድምፅ ። 3. ጉምጉምታ።

ተጉረመረመ ግ የነጎድጓድ ድምፅ ተሰማ።

አጉረመረመ ግ 1. የነጎድጓድ ድምፅ አሰማ(ሰማይ)። 2. ጮሀ፣ ተንጓጓ(ሆድ)። 3. ዝቅ ባለ ድምፅ የቅሬታ አነጋገር ተናገረ፣ አጉተመተመ።

ጎረመሰ ግ 1. ጎረምሳ ሆነ። 2. አበሻጋሪ ወይም ጥጋበኛ ሆነ(ለወጣት ልጅ)።

ጉርምስና ስ ከ14 18 አመት ያለው የወንድ ልጅ እድሜ።

ጎረምሳ ስ ከ14-18 ገደማ ባለው የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ ወንድ ልጅ።

ጎረመደ "ግረመደ" ን ተመ.

ጎረምሳ "ጎረመሰ" ስር ተመ.

ጎረሰ ግ 1. ምግብ አፉ ውስጥ ጨመረ። 2. በላ። *ለምቱ ትንሽ ጉረስ አለኝ*። 3. ጠበንጃ፣ሽጉጥ፣... ውስጥ ጥይት ተጨመረ ወይም ገባ። 4. ያዘ። *ባትሪው ስንት ድንጋይ ይጎርሳል።*

ጉርሻ ስ 1. አፍ ውስጥ አንዴ ሊገባ የሚችልና እጅ መጥኖ የሚይዘው የምግብ መጠን። 2. ዳረጎት። 3. ከመደበኛ ክፍያ ወይም ደመወዝ በተጨማሪ የሚሰጥ የገንዘብ ስጦታ። 4. ጉቦ። 5. ምግብ ሲበላ (ለማቅመስ፣ ለማጥገብ፣ ፍቅርን ለመግለፅ፣...) ሲባል አንዱ ለሌላው በእጅ ጠቅልሎ ወደአፉ የሚከትለት ምግብ።

-ጎራሽ -ያህል የሚጎርስ።*ዘጠኝ ጎራሽ ጠመንጃ*።

ጎረበ ግ 1. የውስጥ እጅ ቆዳ በስራ ብዛት የተነሳ ወይም ሌላው የሰውነት ክፍል ቆዳ በበሽታ ምክንያት ውሃ እያቋጠረ ወይም ሳይቋጥር አነፈነፈ፣ ጉብ ጉብ አለ። 2. ተወጥሮ የነበረው ወይም መወጠር ያለበት ነገር ረገበ ወይም ላላ አለ።3. ገለባው ከፍሬው ላይ ሙልጭ ብሎ እንዳይሄድ ለማድረግ በመጠኑ ተፈተገ (ስንዴ፣ ገብስ፣...)። 4. የፈላ ውሃ ውስጥ የገባ አተር፣ ባቄላ፣... ቆዳው ተጨማደደ።

ተጉረበረበ የ"ጎረበ" ን 1ኛ ፍቺ ተመ.

አጉረበረበ ዝ.ከ.

አጎረበ ዝ.ከ.

***ጎረበተ**

ጎረቤት ቅ 1. አቅራቢያ፣ አጠገብ ለአጠገብ፣ ቅርብ ለቅርብ። *እኛና እሱ ጎረቤት ነን*። 2. በአቅራቢያ ወይም በድንበር አካባቢ ያለ (ለምሳሌ ሃገር)። ስ 3. መኖሪያ ቤቱ ከሌላው መኖሪያ አጠገብ ወይም አቅራቢያ የሆነ ሰው። *እሱ ጎረቤቴ ነው።*

ጉርብትና ስ አጠገብ ለአጠገብ ወይም ቅርብ ለቅርብ በሚኖሩ ሰዎች መካከል ያለ ግንኙነት፣ መቀራረብ።

ተጎራበተ ግ አጠገብ ለአጠገብ ወይም ቅርብ ለቅርብ ሆነ።

ተጎራባች ቅ ጎረቤት።

አጎራበተ ግ ጎረቤት አደረገ።

አጎራባች ቅ ወሰንተኛ ጎረቤት።

ጎረበጠ ግ 1. ቆረቆረ፣ አልመች ወይም አልስማማ አለ። 2. አመመ(ሆድን)።

ጎርባጣ ቅ የሚቆረቁር፣ምቾት የሌለው (መቀመጫ፣ መኝታ፣...)።

ጎርበጥባጣ ቅ ወጣ ገባ፣ ያልተስተካከለ።

ጎረነነ ግ ጎርናና ሆነ።

ጎርናና ቅ ወፍራም (ድምፅ)።

ጎረና ግ በአግባቡ ባለመብሰሉና በማረሩ ምክንያት ጣእሙ ተበላሸ (ለምሳሌ ወጥ)።

ጉርናት ስ እንደወጥ የመሰለው በአግባቡ ባለመብሰሉና በማረሩ ምክንያት የሚያመጣው መጥፎ ቃና ወይም ጣእም።

ጎረንጎሬ ስ ከቆዳ የሚሰራ ስለት ያላቸው እቃዎች መከተፊ።

ጎረደ ግ 1. ቆረጠ፣ ጎመደ። 2.ዘለለ፣ ገደፈ (ፊደልን)።

ጉራጅ ቅ ቁራጭ፣ ጉማጅ።

ጉርድ ስ 1. የደረሰኝ ቀሪ ካርኒ። 2. ሙሉ ያልሆነ።

ጉርድ ሸሚዝ ስ እጅጌው አጭር የሆነ ሸሚዝ።

ጉርድ ቀሚስ ስ ከወገብ በታች ያለውን የሰውነት ክፍል ብቻ የሚሸፍን የሴት ቀሚስ ።

ጉርድ ፎቶ ስ ከወገብ በላይ ያለውን የሰውነት ክፍል ብቻ የሚያሳይ ፎቶግራፍ።

ጉርዶሽ(ጉርዶ) ስ ተጀምሮ ሳያልቅ የቀረ ስራ።

ጎራዳ ቅ አፍንጫው አጭርና ትንሽ የሆነ፤ ፉንጋ።

አጉራዶ ስ ባጭር ባጭሩ የተቆረጠ ግንድ።

***ጎረደደ**

ጎርዳዳ ቅ ጆንጎን፥ቀንጎን።

ጎርደድ ጎርደድ አለ ግ በቀስታ በመራመድ ወዲያና ወዲህ ተመላለሰ።

ተንጎራደደ ዝ.ከ.

አንጎራደደ ግ እያሯሯጠ ደበደበ(በዱላ፥ በፍልጥ፥...)።

ጎረደማን(ጎረዶማን) ስ በጋማ ከብት ጀርባ ላይ ሸቀጡን እያስጫነ ከሚያገኙበት ነጋዴ ጋር እየተጓዘ ጭነቱን በመጫን፥ በማራገፍ፥ ከብቶቹን በመንዳት፥... አገልግሎት ይሰጥ የነበረ የሲራራ ነጋዴ አሽከር።

ጎረጎማ ቅ የተሸራረፈ ወይም የወላለቀ (ጥርስ)።

ጎረጎረ ግ 1. ሰረሰረ። 2. በጣት፥ በሳር፥ በላባ፥... የጆሮን፥ የአፍንጫን፥... ውስጥ ነካካ ወይም አከከ። 3. ፈተሸ፥ በረበረ።

ጎረጎደ "ጎደጎደ"ን ተመ.

ጎረጠ ግ ፈጠጠ፥ ወጣ (አይን)።

ጉርጥርጥ(ጎረጥራጣ) ቅ አይነ ፈጣጣ።

ጎሪጥ ዝ.ከ.

የጎሪጥ አየ በንቀት፥ በጥላቻ፥...አየ፤ የጎድን አየ።

ተጉረጠረጠ ግ በቁጣ፥ በንዴት፥... ምክንያት አይኑ ፈጦ ወዲያና ወዲህ ተንከባለለ።

አጉረጠረጠ ግ በቁጣ፥ በንዴት፥... ምክንያት አይኑን በማፍጠጥ ወዲያና ወዲህ አንከባለለ።

ጎረጎጨ ግ ጉሮሮው አካባቢ ድምፅ በማሰማት ጠጣ፤ ጎርጎጭ አደረገ።

ጉርጉጭታ ስ ፈሳሽ ነገር ሲጠጣ ጉሮሮ አካባቢ የሚሰማ ድምፅ።

ጉርጉጭ አደረገ ግ የተጎነጨውን በጉሮሮው አወረደ።

ጎርጎጭ አደረገ ዝ.ከ.

ጎረፈ ግ 1. ድፍርስ ውሃ መሬት ለመሬት በብዛት ፈሰሰ፤ወረደ(በዝናብ የተነሳ)። 2. በብዛት ፈሰሰ (ደም፥እንባ፥...)።3.በብዛት ተመመ፥ ተዥጎደጎደ። *ህዝቡ ወደ ስብሰባው ይጎርፋል።* 4. በብዛት ቀረበ። *ግብዣው ጎረፈ / ጥያቄው ጎረፈ።*

ጎርፍ ስ 1. በብዛት የሚፈስ የዝናብ ውሃ።2. ብዙ አያሌ።

አጎረፈ ግ 1. ጎርፍ ሆነ (የጣለው ዝናብ)። 2. አረፋ ሆነ ወይም አረፋው በደንብ እንዲታይ አደረገ (ልብስ በሳሙና ሲታጠብ)።

ጎሪጥ "ጎረጠ" ስር ተመ.

ጎራ^{1} ስ 1. ከፍተኛ ቦታ፥ ኮረብታ። 2. ፊና፥ ወገን። *ሁሉም በጎራው ተሰልፏል።*

ጎራ^{2}

ጎራ አለ ግ እግረ መንገዱን ደረስ ወይም ገባ አለ (ወደ ሌላ ቦታ በመሄድ ላይ ያለ ሰው)።

ጎራ ግ ከመረ፥ ቆለለ (ድንጋይን፥ እንጨትን፥...)።

ጎራዳ "ጎረደ" ስር ተመ.

ጎራዴ ስ ቅርፁ ጎበጥ ብሎ ረዘም ያለና በአንድ በኩል ብቻ ስለት ያለው ባለእጀታ የጦር መሳሪያ።

ጎሬ ስ ዋሻ፥ ጉድጓድ።

ጎርምጥ^{1} ስ እግር አካባቢ የሚወጣና በቀላሉ የማይድን ከባድ ቁስል።

ጎርምጥ^{2} ስ በባህር ውስጥ የሚገኝ ባለ ብዙ እግር ነፍሳት።

ጎርበጥባጣ "ጎረበጠ" ስር ተመ.

ጎርባጣ ዝ.ከ.

ጎርናና "ጎረነነ" ስር ተመ.

ጎርዳዳ "*ጎረደደ" ስር ተመ.

ጎርፍ "ጎረፈ" ስር ተመ.

ጎሰመ ግ 1. ጎነጠ፥ መታ፥ ወጋ። 2. ደለቀ፥ መታ(ከበሮን፥ ነጋሪትን)።

ጎሰረ ግ ጠቀጠቀ፥ አመቀ፥ አጨቀ። 2. በብዛት አፉ ውስጥ ጨመረ።

ጉሰር ቅ ቀዝር።

ተጎሰረ ግ ተቆዘረ።

ጎሰቆለ ግ ተጎሳቆለ።

ጎስቋላ (ጉስቁል) ቅ የከሳ፥ የመነመነ፥ የተጎዳ(በችግር፥ በሃዘን)።2 በአለባበሱ ቆሸሽ ያለ፥ችግረኛ።

ተጎሳቆለ ግ 1. ከሳ፥ መነመነ፥ ገረጣ(በችግር፥ በሃዘን ምክንያት)።2. በችግር ምክንያት አለባበሱ ቆሸሽ አለ። 3. በደንብ ካለመያዝ የተነሳ ተበላሸ፥ ተንገላታ(ልብስ፥ እቃ፥...)።

ጎሰጎሰ ግ 1. በብዛት ጠቀጠቀ፥ አመቀ፥ ከተተ። 2. (ዘይ.) በብዛት በላ።

ጎሳ ስ የባህልና የቋንቋ አንድነት እንዲሁም በደምና በስጋ ዝምድና ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ያለውና መጠኑ ከነገድ አነስተኛ የሆነ ማህበረ ህዝብ።

የጎሳ ፖለቲካ ስ በዘር፥ በጎሳ፥ በብሄረሰብ ላይ የተመሰረተ ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ።

ጎስቋላ "ጎሰቆለ" ስር ተመ.

ጎሸ ግ ደፈረሰ።

ጉሽ ቅ ድፍርስ ወይም ያልጠራ።

ጉሽ ጠላ ስ ድፍርስ ወይም ያልጠራ ጠላ።

ጎሸመ ግ 1.በክርን ነካ ወይም ገፋ አደረገ፥ጎንተለ፣ መታ። 2."በነገር ጎሸመ"ን ተመ.

ጎሸመጠ ግ 1. በአሽሙር ተናገረ። 2. አሽሟጠጠ።

ጎሽ^{1} ስ ፈርጣማ ጫንቃና አጫጭር እግሮች እንዲሁም ስፋፊ ሆነው ወደታች የተቀለበሱ ጆሮዎች ያሉት፥ የማየትና የመስማት ችሎታው ከፍተኛ የሆነ፥ ከቀንድ ከብት ጋር በቅርብ የሚዛመድ የዱር እንስሳ (ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።

የጎሽ ፀጉር ስ በአንዳንድ ሰዎች ማጅራት ወይም ጆሮ ግንድ ወይም ግንባር አካባቢ የሚበቅል ስስ፥ ለስላሳና ቀላ ያለ ፀጉር።

ጎሽ^{2} 1. እንኳን፡ ጥሩ፡ መልካም፡... ለማለት የሚባል የምስጋናና የማበረታቻ ቃል። *ጎሽ የኔ ልጅ! ጎሽ በርታ!* 2. እባክህ። *ጎሽ መፅሃፉን አቀብለኝ።*

ጎሽ አለ ግ እሰይ፥ እንኳን፥... አለ።

ጎበረ ግ 1. አበጥ ወይም ወጣ ብሎ ታየ። 2. ልጥፍ፥ ልስቅ ሳይል ቀረ፤ ክፈፍ አለ።

ጉብር ስ እንደ ጉጥ ወጣ ብሎ የሚታይ የአንድ ነገር አካል።

ጉብራት ዝ.ከ.

ተጎበረ ግ አበጥ፥ ክፈፍ፥ ጉብ አለ።

አጎበረ ግ ጎበረ።

ጎበረረ ግ በመድረቁ ምክንያት ጎባጣ ሆነ።

ጎብራራ(ጎበረር) ቅ የደረቀና የጎበጠ።

ተንጎበረረ ግ ጎበረረ።

አጎበረረ ዝ.ከ.

አንጎበረረ ግ ጎብራራ እንዲሆን አደረገ፥ አንጎበደደ።

ጎበሰተ ግ በተደጋጋሚ ሳለ፥ ኡሁ ኡሁ አለ።

ጎበበ ግ 1. ልጥፍ ወይም ልስቅ ሳይል ቀረ፤ ኩፍፍ አለ። 2. ጎበጠ።

ጎባባ ቅ ጎባጣ።

ተንጓበበ ግ ጎበበ።

አንጓበበ ግ ጎንባሳ ወይም ጎባጣ እንዲሆን አደረገ።

ጎበኘ ግ ተዘዋውሮ አየ ወይም ተመለከተ።

ጉብኝት ስ ስለአንድ ነገር ወይም ቦታ ለማወቅ፥ ለመረዳት ወይም ለማድነቅ እየተዘዋወሩ የማየት ወይም የመመልከት ድርጊት።

ጎብኚ ስ ታሪካዊ ቦታዎችን ወይም ሌሎች ነገሮችን እየተዘዋወረ የሚያይ ወይም የሚመለከት ሰው።

አስጎበኘ ግ ከጎብኚው ጋር አብሮ በመዞር ስለሚታየው ነገር ለጎብኚው አስረዳ፥ አሳወቀ።

አስጎብኚ ቅ ጎብኚዎችን እየዞረ የሚያሳይ፥ የሚያስጎበኝ።

ጎበዘ ግ ጎበዝ ሆነ።

ጎበዝ ቅ 1. ጀግና፥ ሃይለኛ፥ ብርቱ፥ ጠንካራ። 2. ታታሪ፥ ትጉህ። 3. በአንድ ሙያ ወይም የእውቀት ዘርፍ፥... ጥሩ ችሎታ ያለው።

የጎበዝ አለቃ ስ በጦርነት፥ በአሰሳ ወይም ሌሎች ተመሳሳይ በሆኑ እንቅስቃሴዎች ወቅት በአንድ አካባቢ የሚገኙ ተዋጊዎችን ወይም አሳሾችን እንዲመራ በአካባቢው ሰዎች በችሎታው የሚመረጥ አለቃ ወይም መሪ።

ጉብዝና ስ 1. ጀግንነት፥ ሃይል፥ ብርታት፥ ጥንካሬ። 2. ትጋት፥ ታታሪነት። 3. ጥሩ ችሎታ።

*ጎበደደ

ጎብዳዳ ቅ ጎባጣ፥ ጎንባሳ።

ጉብድድ አለ ግ ጎባጣ ወይም ጎንባሳ ሆነ።

ጎብደድ አለ ግ ጎንበስ አለ።

አጎበደደ ግ 1. ጎበጠ። 2. አጎነበሰ። 3. (ዘይ.) ራሱን ዝቅ በማድረግ ተለማመጠ፥ አሸረገደ።

አጎብዳጅ ቅ ራሱን ዝቅ በማድረግ የሚለማመጥ፥ የሚያሸረግድ፥ አድርባይ።

ጎበጎበ^{1} ግ ጉብጉባት አበጀ።

ጉብጉባት ስ አንድን ነገር ለማስጌጥ ሲባል ጉብ ጉብ እንዲል ተደርጎ የሚሰራ ጌጥ።

ጎበጎበ^{2} ግ ውሃ ያዘ፥ ቋጠረ፥ አጎረበ(የሰውነት ቆዳ)።

አጎበጎበ ዝ.ከ.

*ጎበጎበ

ጉብጉብ ስ የተጎበጎበ ሊጥ።

ተጎበጎበ ግ አብሲት በመብዛቱ ወይም ሊጡ በመቅጠኑ የተነሳ ለማስተካከል ሲባል ሊጡ ላይ ዱቄት በመጨመር ተለወሰ።

አጎበጎበ ግ አብሲት የበዛበትን ወይም የቀጠነ ሊጥን አወፍሮ ለማስተካከል ዱቄት በመጨመር ለወሰ።

ጎበጠ ግ አጎነበሰ፥ ጎበበ፥ የደጋን ቅርፅ ያዘ።

ጎባጣ ቅ የደጋን ቅርፅ ያለው፥ ጎንበስ ያለ።

ጎቢጥ ቅ (ስድብ) ዝ.ከ.

ጎበጥባጣ ቅ ጎርበጥበጣ፥ብዙ ቦታ ላይ ጎባጣነት ያለው።

ጎባባ "ጎበበ" ስር ተመ.

ጎባን ስ ማውንት።

ጎባጣ "ጎበጠ" ስር ተመ.

ጎብራራ "ጎበረረ" ስር ተመ.

ጎብኚ "ጎበኘ" ስር ተመ.

ጎብዳዳ "*ጎበደደ" ስር ተመ.

ጎተራ ስ 1. ከጭቃ ወይም ከእንጨት ወይም ከቆርቆሮ፣... አራት ማእዘን ወይም ክብ ሆኖ የሚሰራና ክዳን ያለው የእህል ማስቀመጫ። 2. (ዘይ.) ብዙ የሚበላ፣ ሆዳም።

ጎተራ 1ኛ ፍቺ

ጎተተ(ገተተ) ግ 1. ሳበ፣ ወደ ራሱ አቀረበ። 2. ወደኋላ አስቀረ፣ አዘገየ፣ እንዳይፈጥን አደረገ። 3. የማይፈለግን ጉዳይ፣ ሰው፣ ነገር፣... አስከትሎ ወይም ይዞ መጣ። *የማልፈልገውን ነገር አትጎትትብኝ* ። 4. ጠራ(ሰይጣንን)።

ጎታታ(ጉትት) ቅ ሲሄድ፣ ሲሰራ፣... ፍጥነት፣ ቅልጥፍና የሌለው፣ ቀርፋፋ።

ጎታች ቅ ፍጥነትን፣ እድገትን፣...ወደኋላ የሚያስቀር፣ የሚያዘገይ።

ጎታች ባህል ስ ለእድገት፣ ለዘመናዊ ስልጣኔ፣.. እንቅፋት የሆነ ባህል።

ተጎተተ ግ ዝግ ወይም ቀስ አለ፣ ተንቀረፈፈ።

ተጎታች ስ ተሳቢ(የመኪና)።

ተጓተተ ግ 1. በታሰበው ጊዜ ሳይከናወን ወይም ሳይፈፀም ቀረ። 2. አብሮ ተያይዞ ወይም ተግተልትሎ መጣ ወይም ሄደ።

አጓተተ ግ በታሰበው ጊዜ ሳይፈፀም ወይም ሳይከናወን እንዲቀር አደረገ (አንድን ጉዳይ)።

***ጎተነ**

ጉተና ስ አጠር ያለ ጎፈሬ።

አጎተነ ግ አጠር ያለ ጎፈሬ አሳደገ።

ጎተጎተ ግ አንድ ነገር እንዲደረግ ወይም እንዲፈፀም፣...በተደጋጋሚ በትጋት አሳሰበ፣ ወተወተ፣ ቀሰቀሰ።

ጎትጓች ቅ አንድ ነገር እንዲደረግ ወይም እንዲፈፀም፣...በተደጋጋሚ በትጋት የሚያሳስብ፣ የሚያስታውስ።

ጎታ ስ ከጭቃ ወይም ከእንጨት ወይም ከቀርከሃ የሚሰራና ከጎተራ አነስ ያለ የእህል ማስቀመጫ።

ጎታታ "ጎተተ" ስር ተመ.

ጎታች ዝ.ከ.

ጎትጓች "ጎተጎተ" ስር ተመ.

ጎቸ ግ በትንሽ በትንሹ ከመሬት ቆለለ፣ ቆጭ ቆጭ አደረገ።

ጉች አለ ግ 1. በትንሹ ተቆለለ። 2. ቆጭ አለ፣ ተቀመጠ።

ጉች ጉች ያለ ጡት ቀጥ፣ ፈርጠም ብሎ የሚታይ ያልወደቀ ጡት።

ጎነቆለ(ቆነጎለ) ግ ውሃ ውስጥ የተነከረ ባቄላ፣ አተር፣ ሽንብራ፣...መብቀል ጀመረ።

ጉንቁል ቅ ውሃ ውስጥ ተነክሮ የበቀለ (አተር፣ ባቄላ፣ ሽንብራ፣...)።

አጎነቆለ ግ 1. ጎነቆለ። 2. እንዲጎነቁል አደረገ(ጥራጥሬን ውሃ ውስጥ በመንከር)።

***ጎነበ**

ተጎናነበ ግ ተከናነበ፣ ተጀቦነ፣ ተሸፋፈነ።

***ጎነበሰ**

ጎንባሳ(ጉንብስ) ቅ ጎባጣ።

በጉንብሱ ሄደ አጎንብሶ ወይም ጎብጦ ብሎ ሄደ።

ጎንበስ ቀና አለ 1. ለፋ፣ ደከመ። 2. ተሽቆጠቆጠ። *ጎንበስ ቀና ብሎ አስተናገደኝ*።

ጎንበስ አለ ግ 1. ጎበጥ ወይም ጎብደድ አለ። 2. አንገቱን ዘንበል ወይም ደፋ አደረገ። 3. ከአንገቱ፣ ከትከሻውና ከወገቡ ወደ መሬት ዘንበል ብሎ ዝቅ አለ።

ተጎነበሰ ግ ከአንገቱ፣ከትከሻውና ከወገቡ ወደ መሬት ዘንበል ብሎ ዝቅ አለ፣ አጎነበሰ።

ተጎናበሰ ግ ጎንበስ በማለት ይቅር ተባባለ፣ ታረቀ።

አጎነበሰ ግ 1. ጎንበስ አለ። 2. ራሱን ዝቅ በማድረግ ተለማመጠ፣ አሸረገደ።

አጎንባሽ ቅ አጎብዳጅ።

ጎነተለ ግ ጎነጠ፣ ጎሸም አደረገ።

ጉንተላ ስ ጉንጣ፣ጉሸማ።

***ጎነዘለ**

ጎንዛላ ቅ ዘንፋላ።

ተጎናዘለ ግ ተዘናፈለ።

አጎናዘለ ግ አዘናፈለ።

ጎነደ ግ እራሱን ችሎ ለብቻው መኖር ጀመረ።

ጎናዴ ቅ ለብቻው ኗሪ፣ ላጤ።

ጎነደለ ግ ቆረጠ።

ጎንዳላ(ጉንድል) ቅ ቆራጣ።

ጎነደበ ግ ቆረጠ፣ ጎረደ፣ ጎመደ።

ጎነደሸ ግ ቆረጠ፣ ቆመጠ።

ጉንድሽ ቅ (ስድብ) ቆራጣ፣ ቆማጣ (እጅ

ወይም እግር)።

ጎነጎነ ግ 1. ሶስት ወይም ከዛ በላይ የሆኑ ገመዶችን ወይም ክሮችን፥... በአንድነት እያጠላለፈ ገመደ። 2. የፀጉር ጉንጉን ሰራ።3. (ዘይ.) ነገርን ወይም ሴራን አውጠነጠነ፥ ዶለተ።

ጉንጉን ስ የተጎነጎነ (ፀጉር፥ ቃጫ፥...)።

ጉንጉን አበባ ስ የ"አበባ ጉንጉን"ን ተመ.

ጎነጠ ግ 1. ወጋ (በጣት፥ በእንጨት፥...)። 2. (ዘይ.) በነገር ነካ ወይም በአሽሙር ተናገረ። *በነገር ጎነጠኝ።*

***ጎነጨ**

ጉንጭ ስ ከአይን በታችና ከአፍ ግራና ቀኝ በኩል የሚገኝ የሰውነት ክፍል (ስእሉን ራስ ስር ተመ.)።

ጉንጭ አልፋ ንግግር ፍሬ የሌለው አሰልቺ ንግግር።

ጉንጫሜም ቅ ጉንጩ ወፍራም የሆነ (ሰው)።

ጎንጩት(ጉንጭት) አደረገ ግ አፉ የሚችለውን ያህል ላንዴ ጠጣ።

ተጎነጨ ግ 1. ዝ.ከ. 2. ጠጣ(መጠጥን)።

***ጎነፀፈ**

ተጎናፀፈ ግ 1. መላ ሰውነቱን ሸፈነ (ለምሳሌ በልብስ፥ በመጎናፀፊያ)። 2. በለበሰው ልብስ ላይ ደርቦ ለበሰ(ካባን፥ካፖርትን፥...)። 3. (ዘይ.) ተቀዳጀ፥ አገኘ(ክብርን፥ ድል፥...)።

መጎናፀፊያ(መጎናጠፊያ) ስ የዕላት መሸፈኛና መሸከሚያ የሆነ ረጅምና ሰፊ ግምጃ።

አጎናፀፈ ግ 1. አለበሰ፥ ሸፈነ። 2. አቀዳጀ፥ ሰጠ (ክብርን፥ ድልን፥...)።

ጎነፈ ግ 1. የለበሰውን ልብስ በጉያው ወይም በብብቱ ወደ ላይ ሰብስቦ ያዘ።2. አፈነ፥ ሸፈነ(በጪስ)። 3. አፈር አስታቀፈ(ተክልን)። 4. በሙቅ ውሃ ዘፍዝፎ አጠበ(ልብስን ወይም ማንኛውንም እቃ)። 5. በረመጥና በውሃ አጠበ(በቅባት የተበከለን እቃ)።

ጉንፍ ስ በብብት አካባቢ ያለ የሰውነት ክፍል፥ ጉያ።

ጎናም "ጎን" ስር ተመ.

ጎናዴ "ጎነደ" ስር ተመ.

ጎን ስ 1. በሰውነት ግራና ቀኝ በኩል የሚገኝና ከብብት እስከ ዳሌ ድረስ ያለው የሰውነት ክፍል። 2. በስተቀኝ ወይም በስተግራ በኩል የሚገኝ የማንኛውም አካል፥ ነገር ክፍል።

ከጎንህ ታገኘዋለህ ያደረግከው ወይም የምታደርገው ነገር መጥፎ ውጤት ያስከትልብሃል ለማለት የሚነገር የማስጠንቀቂያ ወይም የዛቻ አነጋገር።

ወደጎን ተጠመዘዘ /ታጠፈ ወደ ቀኝ ወይም ወደ ግራ በኩል ተጠመዘዘ።

የጎን ቁጥር ስ በህዝብ ወይም በጭነት ማመላለሻ መኪናዎች ጎን ላይ ከታርጋ ቁጥር በተጨማሪ የሚፃፍ መለያ ቁጥር።

የጎን ንግግር አሽሙር።

የጎን ውጋት ሆነበት በጣም ነዘነዘው፥ ጨቀጨቀው፥ ፋታ ነሳው።

ጎን ለጎን አጠገብ ለአጠገብ።

ጎናም ስ ጎኑ ሰፊ የሆነ።

ጎንባሳ "*ጎነበሰ" ስር ተመ.

ጎንዛላ "*ጎነዘለ" ስር ተመ.

ጎንዳላ "ጎነደለ" ስር ተመ.

ጎኘረ ግ 1. ነፋ፥ ቆዘረ(ለሆድ)። 2. አጨቀ፥ ጠቀጠቀ፥ ሞላ(ከረጢትን)።

ጉኘር ቅ ቀገር።

ጎዘጎዘ ግ 1. ነሰነሰ፥ በተነ፥ አነጠፈ(ሳርን፥ ቅጠልን፥...)። 2. አነጠፈ፥ ደለደለ፥ ጉዝጓዝ አደረገ(ለመኝታ፥ለመቀመጫ፥...)።

ጉዝጓዝ ስ 1. በቤት፥ በድንኳን፥ በዳስ፥... ወለል ላይ የሚነሰነስ፥ የሚነጠፍ ሳር፥ ቄጠማ ወይም ቅጠል። 2. ምቾት እንዲኖረው በመኝታ ወይም በመቀመጫ ላይ የሚደረግ ድልዳል።

ጎደለ ግ 1. ፊት የነበረውን ያህል ሳይሆን ቀረ፥ ሙሉ የነበረው መጠኑ ቀነሰ ወይም አነሰ። 2. የሚፈለገውን ያህል ሳይሆን፥ ሳይሞላ፥ ሳይገኝ ቀረ፥ መጠኑ ወይም ብዛቱ አነሰ።

ጉድለት ስ 1. እንከን፥ ስህተት። 2. ማነስ፥ መቀነስ፥ መጉደል። *ገንዘቡ ሲቆጠር ጉድለት አሳየ።* 3. እጥረት። *የቫይታሚን ጉድለት።*

ጎደሎ(ጎዶሎ) ቅ 1. ሙሉ ያልሆነ፥ የተቀነሰለት፥ ያልተሟላ። 2. የሰውነት ክፍሉ ወይም አካሉ ያልተሟላ(እጁ ወይም እግሩ የተቆረጠ፥ አይኑ የጠፋ፥..)። 3. (ዘይ.፥ስድብ) አጭር፥ ኩሩሩ።

ጎደሎ ቀን ስ መጥፎ አጋጣሚ(አደጋ፥ ሞት፥...) የደረሰበት ወይም ያጋጠመበት ቀን።

ጎደሎ ቁጥር ስ ለሁለት ሲካፈል ቀሪ የሚኖረው ቁጥር (ለምሳሌ 3፥5፥ 9፥ 11...)።

ተጓደለ ግ 1. ሲደረግ የነበረው ወይም የተለመደው ነገር ተቋረጠ፥ ቀረ፥ ተስተጓጎለ። 2.ሳይሟላ ቀረ፥ ጎደለ።

አጎደለ ግ 1. ካለው ወይም ከነበረው ነገር ላይ አነሳ፥ ቀነሰ። 2. (የሆነ ሰው ወይም እቃ) ባለመኖሩ ወይም ባለመገኘቱ የተነሳ መከናወን፥ መፈፀም፥... የሚገባው ነገር ሳይከናወን ወይም ሳይፈፀም ቀረ፥ አጎዳ።

ጎደራ ግ ሙሁ፣ አገሳ (ለምሳሌ አንበሳ)።

ጎደሬ ስ ስሩ እንደ ድንች ከመሬት ተቆፍሮ የሚወጣና የሚበላ ቅጠሉ ሰፋፊ ተክል።

ጎደበ ግ 1. ጉድባ ሰራ። 2. አድፍጦ ጠበቀ።

ጉድባ ስ 1. ፈፋ፣ ጉድጓድ። 2. ምሽግ።

***ጎደኘ**

ተጎዳኘ ግ 1. (በስራ፣በአላማ፣...) አብሮ ሄደ ወይም ተጓዘ፤ ተወዳጀ። 2. ተጣመረ።

አጎዳኘ ግ 1. (በስራ፣ በአላማ፣...) አብሮ እንዲጓዝ ወይም እንዲሄድ አደረገ፤ አወዳጀ። 2. አጣመረ።

***ጎደደ**

ጎዳዳ ቅ ጅንን፣ ኩሩ።

ተጓደደ ግ ኮራ፣ ተጀነነ፣ ታበየ።

ጎደጎደ(ጎረጎደ) ግ 1.ጥልቀት ኖረው፤ ጉድጓድ ሆነ። 2. ዝርግ የሆነ ወይም ሞላ ወይም ወጣ ያለ ነገር ወደ ውስጥ ገባ፣ ተሰረጎደ።

ጉድጓድ ስ ወደ ታች ተቆፍሮ ወይም ተምሶ ክፍት የሆነ መሬት።

ጉድጓድ ገብተህ ታመጣለህ ከየትም ፈልገህ ታመጣለህ።

ጎድጓዳ ቅ ዝርግ ያልሆነ ወይም ወደ ውስጥ የሰረጎደ።

ጎድጓዳ ሳህን ስ ዝርግ ያልሆነ፣ እንደብረት ድስት የተሰራ ሳህን።

አጎደጎደ ጥልቀት እንዲኖረው አድርጎ ቆፈረ።

***ጎደጎደ**

ነጎድጓድ ስ የመብረቅ ድምፅ ወይም ጉርምርምታ።

ተንጎደጎደ ግ 1. ሙሁ ወይም የነጎድጓድ ድምፅ ተሰማ። 2.ተንገርቀገርቀ፣ በብዛት ፈሰሰ፣ ወረደ። 3. በብዛት ሆነ ወይም ተደረገ።

አንጎደጎደ ግ 1. የነጎድጓድ ድምፅ አሰማ። 2. በብዛት ሰጠ፤ አንጎደጎደ። 3. አወረደ፣ አፈሰሰ። *ዝናቡን ላንጎደጎደው።*

ጎደፈ ግ 1. አደፈ ወይም ቆሸሸ። 2. ጠፋ፣ ተበላሸ (ስም፣ክብር፣ ዝና፣...)።

ጉድፍ ስ ቆሻሻ ወይም ጥራጊ።

አጎደፈ ግ 1. አቆሸሸ። 2. (ዘይ.) አጠፋ፣ አበላሸ(ስምን፣ ክብርን፣ዝናን፣...)።

ጎደፈረ ግ ጫረ፣ ማሰ፣ ቆፈረ።

ጎዳ ስ 1. ቀንድ የሌለው(ከብት)። 2. ጥለት የሌለው(ጋቢ፣ ኩታ፣...)።

ጎዳ ግ 1. ችግር፣ ስቃይ፣ ህመም፣... አስከተለ (አደጋ፣ ዱላ፣...)። 2. በደለ፣ ቅር አሰኘ፣ አስቀየመ። 3. አድሉአዊ በሆነ ወይም ባልተመጣጠነ ወይም ትክክል ባልሆነ፣... ሁኔታ አንድን ነገር አደረገ። *ዳቦውን ሲያካፍል እኔን ጎድቶኛል/ ሜማውን ሲሸጥልኝ በዋጋ ጎድቶኛል።*

ጉዳት ስ 1. ችግር፣ ስቃይ፣ ጉስቁልና(በህመም፣ በአደጋ፣ በሃዘን፣... ምክንያት የሚመጣ)። 2. ትክክል፣ ተገቢ፣ ተመጣጣኝ ባልሆነ ሁኔታ የተፈፀመ ድርጊት። የአንድ ነገር መሰበር፣ መበላሸት፣... ወይም የአካል መጉደል።

ጉዳተኛ ቅ ጉዳት የደረሰበት(ሰው)።

ጎጂ ቅ ጉዳት የሚያስከትል።

ጎጂ ባህል ስ በሰው ላይ ጉዳት የሚያመጣና ኋላቀር የሆነ ባህል፣ ልማድ።

ተጎዳ ግ የቅርብ ዘመድ ሞተበት። *ለገሌ ላባቱን ተጎዳ።*

አጎዳ ግ (የሆነ ሰው ወይም እቃ) ባለመኖሩ ወይም ባለመገኘቱ የተነሳ መከናወን ወይም መፈፀም የሚገባው ነገር ሳይከናወን ወይም ሳይፈፀም ቀረ፤ አጎደለ።

ጎዳና ስ መንገድ።

ጎዳዳ "ጎደደ" ስር ተመ.

ጎድን ስ 1. ዘግራና በቀኝ በኩል ከአከርካሪ አጥንት እስከ ደረት አግድም የሚዘረጋና በቀኝ አስራ ሁለት በግራ አስራ ሁለት ሆኖ የሚገኝ የደረት አጥንት። 2. ጎን። 3. ጎድን! እንዳይገፋህ ወይም ዞር በል ለማለት የሚነገር ቃል(የተጫነ አህያ በሰዎች አጠገብ በሚተላለፍበት ጊዜ)።

የጎድን አየ 1. ገረመመ። 2. ገላመጠ።

ጎድን ጥብስ ስ ለምግብነት ከነአጥንቱ ተጠብሶ የሚዘጋጅ የከብት ጎድን።

ጎድጓዳ "ጎደጎደ" ስር ተመ.

ጎደሎ "ጎደለ" ስር ተመ.

ጎጂ "ጎዳ" ስር ተመ.

ጎጆ ስ 1. ጎጆ ቤት። 2. (ዘይ.) የትዳር ኑሮ።

ጎጆ ቀለሰ 1. ጎጆ ቤት ሰራ። 2. ትዳር መሰረተ።

ጎጆ ወጣ 1.ትዳር መሰረተ። 2. እራሱን ችሎ ለብቻው መኖር ጀመረ (ከነሚስቱ ከወላጆቹ ጋር ይኖር የነበረ)።

ጎጆ መውጫ ሳልተደራጀና የራሱን ቤትና ትዳር ገና ለሚመሰርት ሰው የሚሰጥ ማቋቋሚያ(ገንዘብ፣ እቃ፣...)።

ጎጆ ወጪ 1. አዲስ ትዳር መስራች። 2. እራሱን ችሎ ለብቻ መኖርን ገና የጀመረ።

ጎጆ አወጣ ለአንድ ሰው ገንዘብ፣ እቃ፣... በመስጠት ራሱን እንዲችል ወይም እንዲቋቋም አደረገ።

ጎጆ ቤት ስ አነስተኛ የሳር ቤት።

ጎጆ ቤት

የጎጆ ኢንዱስትሪ ስ እንደ ፋብሪካ ውስብስብ ቴክኖሎጂና የማምረቻ መሳሪያዎችን ሳይጠቀም በቤት ወይም በመኖሪያ አካባቢ ተወስኖ ልዩልዩ የፍጆታና የአገልግሎት ውጤቶችን የሚያመርት አነስተኛ ኢንዱስትሪ።

ጎጠረ ግ ነፋ፣ ቀበተተ(ሆድን)።

ጉጥር ቅ (ስድብ) ሆዱ የተነፋ ወይም ጉስር ያለ።

ጎጠጎጠ ግ ወጋ፣ወጋ አደረገ። *በጣቱ ጎጠጎጠው።*

***ጎጠነጠ**

ጉጥ ስ 1. በእንጨት ላይ እንደ ጡት ጉብ ጉብ ብሎ የሚታይ የእንጨቱ ክፍል። 2. በማንኛውም ነገር ላይ አበጥ ወይም ጉብ ብሎ የሚታይ አካል።

አጎጠነጠ ግ 1. መውጣት ወይም ማደግ ጀመረ(ጡት)። 2. አበቀለ፡ አጎመጎመ(ተክል ላይ የሚወጣ ጉጥ)።

አጎጠጎጤ ቅ ጡቶቿ ቆም ቆም ማለት የጀመሩ ወይም ለአካለ መጠን የደረሰች (ልጃገረድ)።

አጎጤ ቅ 1. አጎጠጎጤ። 2. ቆም ቆም ማለት የጀመረ ጡት።

ጎጥ ስ 1. ጉብታ፡ ኮረብታ። 2. መንደር።

ጎፈረ ግ አደገ ወይም እንደ ጎፈሬ ሆነ(ፀጉር)።

ጎፈሬ ስ ተከርክሞና ተበጥሮ ቀጥ ብሎ የሚቆም ፀጉር

ጎፈር ስ 1. የአንበሳ ወይም የዝንጀሮ ጋማ ወይም ፀጉር። 2. እንደ ቆብ ተዘጋጅቶ በራስ ላይ የሚጠለቅ የአንበሳ ወይም የዝንጀሮ ፀጉር ። 3. ከአንበሳ ቆዳ የተዘጋጀ ለምድ።

አጎፈረ ግ ፀጉሩን እንደ ጎፈሬ አሳደገ።

ጎፈነነ ግ አንገሸገሸ፣ አንገፈገፈ(ጣእም)።

ጎፍናና ቅ የሚያንገሸግሽ፡ ጎምዛዛ (ለጣእም)።

ጎፈየ ጉፋያ ሆነ።

ጉፋያ ቅ 1. የማይታኘክ፣ አንጀ(ስጋ)። 2. የከሳና ያረጀ (ከብት)። 3. (ዘይ.፣ስድብ) ያረጀ፣ የሸመገለ(ሰው)።

ጎፈጎፈ ግ አረጀ፣ ሸመገለ።

ጎፍጓፋ ቅ (ስድብ) ያረጀ፣ የደከመ።

ጎፈጠጠ ግ በእርጅና ወይም በህመም ምክንያት ጎበጠ።

ጎፍጣጣ(ጉፍጥጥ) ቅ (ስድብ) ያረጀ፡ የደከመ።

ተንጎፈጠጠ ግ ጎፈጠጠ።

ጎፈጨረ ግ በጥፍሩ ጫረ፡ ሟጨረ፣ ቧጠጠ።

***ጎፈፈ**

ጎፋፋ ቅ ቀርፋፋ፣ ቅልጥፍና የሌለው፡ ጎታታ።

ተንጓፈፈ ግ በአለባበሱ ዝርክርክ ብሎ እየተጎተተ ወይም እየተንቀረፈፈ ተራመደ፣ ሄደ።

ጎፋ ግ በረገገ፣ ወገሸ።

ጎፍላ^{1} ስ በሞተ ጥጃ ቆዳ ውስጥ ገለባ በመጠቅጠቅ የሚሰራ የጥጃ ምስል።

ጎፍላ^{2} ስ በሸንጥ ማህደር፣ በመጎናፀፊያ፣... ዙሪያ የሚገኝ የክር ወይም የሃር ወይም የሱፍ ዘርፍ።

ጎፍናና "ጎፈነነ" ስር ተመ.

ጎፍጓፋ "ጎፈጎፈ" ስር ተመ.

ጎፍጣጣ "ጎፈጠጠ" ስር ተመ.

ጓ^{1} የ "ግ" ፊደል ፍንፅቅ ዘር።

ጓ^{2}

ጓጓታ ግ በመተረማመስ ወይም በመጋጨት የሚሰማ ድምፅ።

ጓ አለ ግ እንደ በርና መስኮት ያለ ነገር ሲጋጭ የሚሰጠውን ድምፅ አይነት ሰጠ።

ጓጓ አለ ግ ተንጓጓ።

ጓጓ አደረገ ግ አንጓጓ።

ተንጓጓ ግ በመተረማመስ ወይም በመጋጨት በተደጋጋሚ ጓ ጓ የሚል ድምፅ ሰጠ።

አንጓጓ ግ በማተረማመስ ወይም በማጋጨት በተደጋጋሚ ጓ ጓ የሚል ድምፅ እንዲሰጥ አደረገ።

ጓል(ጉል) ቅ ያልደቀቀ፣ አንኳር (የአፈር፣ የስኳር፣ የጨው፣...)።

***ጓመጠ**

አንጓመጠ ግ ባፉ ሙሉ ጎርሶ አኘከ ወይም አላመጠ።

ጓሚያ ስ 1. ያልበሰለ ወይም ገና ጥሬ የሆነ(ፍራፍሬ)። 2. ከጮርቃነት ያለፈና በቃሪያነት ደረጃ ላይ ያለ ፍራፍሬ።

ጓሮ ስ በቤት ጀርባ ያለ ቦታ።

የጓሮ አትክልት ስ እንደ ሸንኩርት፣ ጎመን፣ ድንች ያሉና በቤት አካባቢ የሚተከል አትክልት።

ጓሳ ስ ለገመድ፣ ለቤት ክዳን፣ ለወፍጮ

መጥረጊያ፥... የሚያገለግልና በደጋ አካባቢ የሚገኝ ቀጭንና ሸካራ የሳር አይነት፡፡

ጓኑ ግ ወደ ላይ ተወረወረ፤ ነጠረ።

አጓኑ ግ ወደ ላይ ወረወረ ወይም አነጠረ፡፡

ጓንት

ጓንት ስ በእጅ ቅርፅ ከላስቲክ ወይም ከሱፍ ወይም ከቆዳ፥... የሚሰራና ለእያንዳንዱ ጣት ማስገቢያ ያለው የእጅ ሽፋን፤የእጅ ሹራብ፡፡

ጓንዴ ስ ስድስት ጥይት የሚጎርስ አፈ ጭልጭም የጠመንጃ አይነት፡፡

***ጓዘ**

ጉዞ ስ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ በእግር ወይም በሌላ የመጓጓዣ አይነት የሚደረግ እንቅስቃሴ።

ጉዞ ፍታት ስ (ኢ. .ኦ. ተ. ቤ .) አስከሬን ከቤት ወጥቶ መቃብር ቦታ እስኪደርስ ድረስ ሰባት ቦታ ላይ እያረፈ ለሰባት ጊዜ የሚደረግለት የፀሎተ ፍትሃት አይነት።

ጓዝ ስ አብሮ ያለ ወይም የሚኖር ብዙ እቃ፤ ኮተት ወይም ቤተሰብ።

ጓዙን ጠቀለለ ያለውን እቃ ወይም ንብረት ሁሉ ጠቅልሎ ለመሄድ ተነሳ፤ ተዘጋጀ።

ተጓዘ ግ 1. ሄደ፥ ተራመደ። 2. ጉዞ አደረገ። 3. ገሰገሰ። *ለስልጣኑ ጎዳና ተጓዘ።*

ተጓዥ ቅ 1. ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለመሄድ የተነሳ ወይም በመሄድ ላይ ያለ። 2. በአንድ ቦታ ረግቶ የማይቀመጥ ወይም መንገድ የሚያበዛ።

ተጓጓዘ ግ ብዛት ያለው እቃ ወይም ሰው ከአንዱ ወደ ሌላው ቦታ ተጭኖ ተወሰደ፥ሄደ።

መጓጓዣ ስ 1. ከቦታ ወደ ቦታ ለመሄድ ወይም ለመንቀሳቀስ የሚያገለግል የጋማ ከብት፥ መኪና፤አውሮፕላን፥... (ስእሉን የሚቀጥለው ገፅ ላይ ተመ.)። 2. በመኪና፥ በአውሮፕላን፥ በመርከብ፥... ለመጓዝ የሚከፈል ገንዘብ።

አጓዘ ግ ብዛት ያለውን እቃ ወይም ሰው ከቦታ ወደ ቦታ ወሰደ።

አጓጓዘ ግ ብዛት ያለውን እቃ ወይም ሰው ከቦታ ወደ ቦታ ወሰደ።

ጓያ ስ በእሸትነቱ ከተመገቡት፥ እሸትም ባይሆን እንኳ እሱን በልቶ በላዩ ላይ ዉሃ ወይም ተልባ ከተጠጣበት ይሰብራል ወይም ያሽመደምዳል የሚባል አተር መሳይ እህል።

ጓደኛ "ጓድ" ስር ተመ.

***ጓደደ**

ተጓደደ ግ ኮራ፥ ተጀነነ (በትእቢት)።

አጓደደ ግ አኮራ፥ ጀነነ።

ጓዳ ስ በዋናው ቤት ውስጥ የሚገኝና ለማንኛውም ቁሳቁስ ማስቀመጫ የሚሆን ልዩ ክፍል።

ጓዳዋን ያውቃል ምስጢሯን፤ ገመናዋን፥ አኗኗሯን ያውቃል።

የጓዳ በር የምስጢር ወይም የስርቆሽ በር።

ጓድ ስ 1. ጓደኛ። 2. በሶሻሊዝም ወይም በኮሚኒዝም ስርአት ውስጥ ያሉ የፖለቲካ አራማጆች እርስ በርሳቸው የሚጠራሩበት የአቶ ወይም የክቡር መተኪያ ስም። 3. ለአንድ ስራ ወይም ተልእኮ የተመደበ ቡድን።

ጓደኛ ስ 1. ባልንጀራ። 2. አቻ፤ ተመሳሳይ (በእድሜ ወይም በሌላ)።3. ወዳጅ።

ጓደኛ አፈራ ጓደኛ አገኘ ወይም አበጀ።

ጓጉንቸር^{1} ስ 1. በአፈርና በድንጋይ ውስጥ የምትኖርና ቆዳዋ ሸካራ የሆነ የእንቁራሪት አይነት።

ጓጉንቸር^{2} ስ ተንጠልጣይ የበር ቁልፍ (ስእሉን ቁልፍ ስር ተመ.)።

ጓጎለ ግ 1. (እንደ ዱቄት ያለ ነገር በውሃ ሲበጠበጥ) በደንብ ሳይሟሟ ወይም ሳይፈርስ ቀረ፤ እልፍ እልፍ እንደኳስ ተድቦልቡሎ ተገኘ።2. በእግር ብዙ ከመጓዝ ወይም ከባድ ስራ ከመስራት የተነሳ በሰውነት ላይ እልፍ እልፍ ሆኖም ተሰማ፥ ሰውነት ጣመነ።

ጓጓላ ግ (በውሃ ከተበጠበጠ እንደ ዱቄት ካለ ነገር ውስጥ እልፍ እልፍ ሳይሟሟ ወይም ሳይፈርስ እየተድበለበለ የሚገኝ ዱቄት።

ጓጎረ ግ ጮሀ፤ አጓራ።

አጓጎረ ዝ.ከ.

ጓጎት "አጓጎት"ን ተመ.

ጓጎጠ ግ 1. በጣት፤ በእንጨት፥... ነካ ነካ ወይም ወጋ ወጋ አደረገ። 2. ለማስታወክ ጉሮሮውን በጣቱ ነካ ነካ አደረገ።3. አስታወከ ወይም አስመለሰ።

አስጓጎጠ ግ አስታወከ ወይም አስመለሰ።

ጓጓ ግ ተመኘ፥ ጎመጀ፤ ፈለገ።

ጉጉ ቅ አንድ ነገር ለማድረግ፤ ለማግኘት፥... ከፍተኛ ፍላጎት ወይም ምኞት ያለው።

ጉጉት ስ ከፍተኛ ፍላጎት ወይም ምኞት።

አጓጓ ግ 1. አማረ፥ በሜት ሳበ። 2. አንድን ነገር በማሳየት ሌላው ሰው እንዲመኝ ወይም እንዲፈልግ አድርጎ አስጎመጀ። 3. አሳሳ።

ጓጓታ "ጓ^{2}" ስር ተመ.

***ጓጠጠ**

ማንጓጠጥ ስ ማናናቅ፤ማጣጣል ወይም ማሽሟጠጥ።

ተንጓጠጠ ግ ተናቀ፤ተሽሟጠጠ።

አንጓጠጠ ግ አናናቀ፥ አቃለለ፤ አዋረደ ወይም አሽሟጠጠ።

ጓፈሰ ግ አደፈ፤ ቆሸሸ (ልብስ)።

አጓፈሰ ግ አቆሸሸ፤ አሳደፈ።

1

2

3

4

5

6

7



8

9

10

1. ብስክሌት
2. አውቶቡስ
3. የቤት መኪና
4. ባቡር
5. ሄሊኮፕተር
6. አይሮፕላን
7. ጀልባ
8. ሞተር ብስክሌት
9. መርከብ
10. ታንኳ

ጠ

ጠ ከ"ግ" ፊደል ዘር ቀጥሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል(ግእዙ ሆሄ)።

ጠሀነነ ግ ጀነነ፤ አኮራ።

ተጠሀነነ ግ ተጀነነ፤ ኮራ።

ጠሆኘ^{1} ግ 1. ተናደደ፤ ተቆጣ፤ ተበሳጨ። 2. መታ፤ ጠለዘ፤ መደወተ።

ጠሆኘ^{2} ግ ፈጨ፤ አደቀቀ።

ጠለለ ግ 1. ጠራ፤ ኩልል አለ፤ ዝቃጩ ወደታች የተጣራው ወደላይ ሆነ። 2. ተጣራ፤ ነጠረ(ወርቅ፤ ብር፤...)።

ጠሊላ ስ የጠለለ አጓት።

ጥሉይ ቅ የጠለለ፤ የተጣራ (ፈሳሽ)።

አጠለለ ግ 1. አጣራ፤ አቀረረ። 2. አተላው ወደታች ዘቅጦ የተጣራው ወደላይ ሆነ።

ማጥለያ ስ ከሸቦ ወይም ከስንደዶ ተታትቶ የሚሰራና ለማጥራያነት ወይም ለማጥለያነት የሚያገለግል ወንፊት መሰል እቃ፤ ወንጠፍት።

***ጠለለ^{1}**

ተንጣለለ ግ 1. በብዛት ፈሰሰ፤ ተኛ፤ ተጥለቀለቀ (ውሃ፤ ደም፤...)። 2. ሰፊ ሆኖ ተሰራ (ቤት፤ ድንኳን፤...)።

አንጣለለ ግ በሰፊት ሰራ፤ ተከለ (ቤትን፤ ድንኳንን፤...)።

***ጠለለ^{2}**

ጠለላ ስ ከለላ፤ ተገን።

ተጠለለ ግ ተከለለ ወይም ዳነ (ከዝናብ፤ ከፀሃይ፤ ...)።

መጠለያ ስ 1. መከላከያ (ከዝናብ፤ ከፀሃይ፤ ...)። 2. መጠጊያ፤ ማደሪያ፤ ማረፊያ ቦታ።

አስጠለለ ግ 1. አስጠጋ፤ ለጊዜው ማረፊያ ወይም ማደሪያ ሰጠ። 2. መጠለያ ወይም ተገን ሆነ። *ዛፉ አያስጠልልም።*

ጠለላ^{1} "ጠለለ" ስር ተመ.

ጠለላ^{2} "*ጠለለ^{2}" ስር ተመ.

ጠለመ ግ ውሃ ውስጥ ሰጠመ፤ ዘቀጠ። 2. ጠፋ፤ ጠልቆ ቀረ።

ጠለሰ ግ ጥላ ጣለ፤ ጠለስ ሆነ።

ጠለስ ስ የፀሃይ ብርሃን በቀጥታ የማያገኘው ወይም የማያርፍበት ቦታ ፤ ጥላ።

ጠለሰመ ግ ጠንቋይ ወይም ደብተራ የሃረግ፤ የሰው ፤... ምስል እያስመሰለ ሳለ ወይም የጥንቁልና ወይም የአስማት ፅሁፍ ፃፈ።

ጠልሰም ስ 1. ከብር ወይም ከሌላ ማእድን ይሰራ የነበረ የሴቶች የአንገት ጌጥ። 2. የተለያየ ስእል ያለበት የጥንቆላና የአስማት ፅሁፍ የያዘ ጥቅል ብራና ወይም ወረቀት።

ጠለስ "ጠለሰ" ስር ተመ.

ጠለሸት "ጥላሸት"ን ተመ.

ጠለቀ^{1} ግ 1. ዘቀጠ፤ ሰጠመ። 2. ወደ ውስጥ ዘልቆ ገባ። 3. በጣም ጎደጎደ። 4. ገባ። *ፀሃይ ጠለቀች።*

ጠላቂ ስ ከባህር ወይም ከወንዝ ውስጥ ጠልቆ የሚገባ ዋናተኛ።

ጣልቃ በመካከል ወይም በማቋረጥ ወይም አልፎ አልፎ (ያለ፤ የገባ፤ የሚገባ፤...)።

ጣልቃ ገባ 1. በማይመለከተው ወይም በማያገባው ነገር ገባ። 2. ያልተራው ወይም ያለቦታው በሌላው መካከል ገባ።

ጣልቃ ገብ ቅ በጣልቃ፤ በመካከል የሚገባ።

ጥልቅ ቅ 1. ወደታች በጣም ርቀት ያለው (ውቅያኖስ፤ ጉድጓድ፤...)። 2. ሰፊና ዝርዝር የሆነ (እውቀት፤ ምርምር፤...)። 3. ስሜትን የሚነካ። *ጥልቅ ሀዘን ተሰምቶታል።*

ጥልቅ መርፌ ስ የጥልፍ መስሪያ የሆነ በጣም ትንሽ መርፌ።

ጥልቀት ስ 1. የወደ ውስጥ ወይም የወደታች ርቀት (የባህር፤ የወንዝ)። 2. ወደታች ወይም ወደ ውስጥ ያለ የርቀት መጠን። *የጉድጓዱ ጥልቀት አንድ ሜትር ነው።* 3. መጠን፤ ስፋት (የእውቀት፤ የምርምር)።

ጥልቅ አለ ግ 1. ዘው አለ ወይም ድንገት ገባ። 2. በማይመለከተው ነገር ውስጥ ገባ። *በሰው ጉዳይ ጥልቅ አትበል።*

ጥልቅ ብዩ ቅ በማያገባው ወይም በማይመለከተው ነገር የሚገባ።

ጠለቀ^{2} ግ ጨለፈ፤ ደነበቀ(ፈሳሽን)። 2. ጨለፈ፤ አወጣ (ውሃን)።

መጥለቂያ ስ ውሃን ወይም ሌላ ፈሳሽ ነገርን ከበርሜል፤ ከእንስራ፤ ከጉድጓድ፤... መቅጃ።

ጠለቀ^{3} ግ ገባ፤ ተደረገ። *የአበባ ጉንጉን በአንገቱ ጠለቀለት።*

አጠለቀ ግ 1. ለበሰ (ለምሳሌ ሹራብ፤ ሱሪ)። 2. አለበሰ (ለሌላ ሰው) ። 3. በብዛት ያዘ፤ አለበሰ። *እስክ አጠለቀው።*

ተጥለቀለቀ ግ በብዛት ተሸፈነ፤ ተሞላ (ለምሳሌ በጎርፍ)።

አጥለቀለቀ ግ በብዛት ሸፈነ፤ አለበሰ፤ሞላ (ለምሳሌ ጎርፍ፤...)።

ጠለንጅ(ጠሌንዥ) ስ ግንዱ አንጓ ያለው አነስተኛ የእፅዋት አይነት።

ጠለዘ ግ መታ፥ ነረተ።

***ጠለጠለ**

ጥልጥል አለ ግ ተንጠለጠለ።

ጥልጥል አደረገ ግ አንጠለጠለ።

ተንጠለጠለ ግ 1. ተሰቀለ። 2. ከፍ ያለ ቦታ ላይ ወጣ፡ ተቀመጠ። 3. አጠረ (ልብስ)። ሊዘንብ ወይም ሊጥል ተቃረበ(ዝናቡ)። 5. ሊወድቅ ወይም ሊፈርስ ትንሽ ቀረው። *ግንቡ ተንጠልጥሏል።* 6. ተጀምሮ ሳያልቅ ወይም ሳይፈፀም ቀረ። *ጉዳዩ እንደተንጠለጠለ ቀረ።*

ተንጠላጠለ ግ ወጣ (ዛፍ፥ ገደል፥...ላይ)። 2. በሰው ድጋፍ ወደ አንድ ደረጃ ተሸጋገረ።

አንጠለጠለ ግ 1. ሰቀለ። 2. በጆሮ ላይ አደረገ(ጌጥን)። 3 በእጁ ያዘ። *ሻንጣውን አንጠልጥሎ ወጣ።* 4. ስሜትን ያዘ፥ ማረከ፥ አጓጓ። 5. ሳይጨርስ በጅምሩ ተወ።

እንጥልጥል ቅ 1. የተንጠለጠለ ወይም ያላለቀ(ጉዳይ) ። 2. ተንጠልጣይ የሆነ፡ (ለምሳሌ የጆሮ ጌጥ)። 3 በአንዳንድ በጎች ወይም ፍየሎች አንገት ላይ ተንጠልጥለው የሚታዩና እንደ ጡት ጫፍ ያሉ አካላት።

ጠለፈ ግ 1. አሰናከለ፥ አወሳከፈ። 2. በጨርቅ ላይ በክር እየሰፋ አስጌጠ፤ የጥልፍ ስራ ሰራ። 3. አድብቶ በሃይል ወይም በማስገደድ ወሰደ (ልጃገረድን ለትዳር)። 4.ነጥቆ ወሰደ፥ ቀማ (አሞራ)። 5.አቅጣጫውን አስለውጦ ወደሚፈለግበት ቦታ ወሰደ (ወንዝን)። 6. አስገድዶ አቅጣጫ አስቀየረ (ብዙውን ጊዜ አውሮፕላንን)። 7. አሰረ(በገመድ)። 8. በሬዲዮ ወይም በስልክ ለሌላ ሰው የሚተላለፈውን መልእክት በምስጢር አደመጠ። 9. የስልክ፥ የኤሌክትሪክ፥... መስመርን ከሌላ መስመር ቀጠለ።

ጠለፋ ስ 1. ከመንገድ አስገድዶ በመውሰድ ሚስት የማግባት ድርጊት። 2. አቅጣጫን መለወጥ (ለምሳሌ የወንዝን አፈሳሰስ)።

የጠለፋ ዋስ ስ ባለእዳን ለማቅረብ ዋስ የሚሆን ሰው።

ጥልፍ ስ በቀሚስ፥ በተለያየ ጨርቅ፥... ላይ በመርፌና በክር ተወሳስቦ የሚሰራ ጌጥ።

ጥልፍ ቀሚስ ስ በጥልፍ የተጌጠ የአበሻ ቀሚስ።

ጥልፍልፍ ቅ 1. ተወሳስቦ የተሰራ (ለምሳሌ ጫማ)። 2. ውስብስብ።

ጥልፍ

ተጠለፈ ግ 1. አቅጣጫው ተለወጠ (የወንዝ አፈሳሰስ)። 2. ተገዶ አቅጣጫ ቀየረ (አውሮፕላን)።

ተጠላለፈ ግ ተያያዘ፥ ተወሳሰበ፥ ተቆላለፈ።

አጠላለፈ ግ አወሳሰበ፥ አቆላለፈ፥ አስተሳሰረ።

ጠላ^1 ስ ከገብስ ወይም ከማሽላ ወይም ከዳጉሳ ወይም ከበቆሎ እንዲሁም ከብቅልና ከጌሾ በቤት ውስጥ የሚዘጋጅ መጠጥ።

ጠላ አነሳ የተጣራውን ወይም የበሰለውን ጠላ ከአተላ እየለየ በሌላ እቃ ቀዳ።

ጠላ ጠመቀ ጠላ አዘጋጀ።

የጠላ ቂጣ ስ በጠላ ጥንስስ ውስጥ የሚገባ ቂጣ።

ጠላ ቤት ስ ጠላ የሚሸጥበት ቤት፤ መሸታ ቤት።

ጠላ^2 ግ አልወድ አለ፡ ጥላቻ አሳየ።

ጠላት ስ 1. የማይወዱት ወይም የሚጠሉት ሰው። 2. ባላጋራ፥ ባላንጣ።3. በአንድ አገር ላይ የዘመተ ወራሪ።

ጠላት አፈራ/ ገዛ ጠላት አበጀ።

ጥል ስ 1. ጠብ ፥ አምባጓሮ፥ ግጭት። 2. ጠበኛ፥ ኩርፍ።

ጥለኛ ቅ የተጣላ፥ ጠበኛ፥ ኩርፈኛ።

ጥላቻ ስ የመጥላት፥ ያለመፈለግ፥ ያለመፍቀድ፥ ፀር የመሆን ስሜት።

ተጠላ ግ የማይወደድ፥ የማይፈቀድ ሆነ።

ተጣላ ግ 1. ጠብ ፈጠረ፡ ተጋጨ፡ ቅራኔ ውስጥ ገባ። 2. አልስማማ አለ፥ አመመ። *የጠጣሁት መጠጥ ተጣላኝ።*

አጣላ ግ ጠብ እንዲፈጠር አደረገ፥ አጋጨ።

አጣይ ቅ ከወዳጅና ከወዳጁ ወሬ እያቀበለ ሰውን የሚያጣላ።

አጥላላ ግ ዋጋቢስ አድርጎ ተናገረ፡ አጣጣለ፥ አራከሰ፥ አናናቀ።

አስጠላ ግ 1. እንዲጠላ አደረገ። 2. አስቀያሚ፥ መጥፎ ሆነ፥ የማይፈቀር ወይም የማይወደድ ሆነ።

አስጠሊታ ቅ የማያምር፡ ደስ የማይል፥ አስከፊ ወይም አስቀያሚ የሆነ።

***ጠላ**

ጥላ ስ 1. ከሰሌን ወይም ከጨርቃ ጨርቅ፥... የሚሰራ የፀሃይና የዝናብ መከላከያ፤ ጃንጥላ። 2. የፀሃይ ጨረር በቀጥታ ያላረፈበት ቦታ። 3. በአንድ አካል ላይ ብርሃን በከፊል ባረፈ ጊዜ ብርሃን ባላረፈበት ወገን በኩል ጥቁር ሆኖ

የሚታይ የአካሉ ምስል። 4. (ዘይ.) መከታ፥ ተገን ። *ሰውዬው የቤተሰቡ ጥላ ነው።*

ጥላ ሆነበት የግብረ ስጋ ግንኙነት የፈፀመ ወይም ከፀሃይ ላይ ቆይቶ የሰውነቱ ሙቀት ገና ያልበረደ፥... ሰው ህመምተኛ ወደተኛበት ክፍል ወይም ቤት ውስጥ ሰለገባ ህመምተኛው ህመም ተቀሰቀሰበት፥ ፀናበት(ለምሳሌ የተገረዘ ህፃን፥ የኩፍኝ፥ ... ህመምተኛ)።

ጥላ በረደ አየሩ ቀዘቀዘ ወይም ሙቀቱ ቀነሰ (ከቀትር በኋላ የፀሃይ ሙቀት እየቀነሰ በመሄዱ)።

ጥላ ነኝ የግብረ ስጋ ግንኙነት የፈፀመ ወይም ከፀሃይ ሙቀት ላይ የቆየ ሰው፥ ቀሰለኛን ወይም ኩፍኝ ወይም ፈንጣጣ፥... የያዘውን ሰው ለመጠየቅ ወደ ህመምተኛው ቤት መግባት እንደማይገባው ለማሳሰብ የሚናገረው አባባል።

ጥላ ጣለ 1. የፀሃይ ግለት በረደ። 2. የፀሃይ ብርሃን በዳመና ወይም በዛፍ ተጋረደ።

ጥላው ቀለለ ቀትረ ቀላል ሆነ፥ ሰውነቱ ሟር አለ።

ጥላ ቢስ ርጋታ የሌለው፥ ከውካዋ፥ ቀትረ ቀላል፥ ግርማ ሞገስ የሌለው ።

ጥላወጊ ስ መተት ወይም አስማት በተደረገበት ሹል ነገር የሰው ጥላ ያረፈበትን ቦታ በመውጋት ሰውየውን ህመምተኛ ለማድረግ ወይም ለመግደል ይችላል የሚባልለት አስማተኛ ወይም ድርጊቱ (መተቱ፥ አስማቱ)።

አጠላ ግ 1. ጥላ ጣለ። 2. ከፀሃይ፥ ከዝናብ ወይም ከብርሃን በጥላ ተከለለ፥ ተጋረደ።

ጠላቂ "**ጠለቀ**^{1}" ስር ተመ.

ጠላት "**ጠላ**^{2}" ስር ተመ.

ጠሌንዥ "**ጠለንጅ**" ን ተመ.

ጠል ስ 1. በሣር ወይም በቅጠል ላይ ተንቆርቁሮ የሚገኝ ርጥበት ወይም ጤዛ። 2. ዝናብ፥ ርጥበት። *ለግዴ ጠል ካወረደ መሬት ይራባል።* 3. ልምላሜ።

ጠልሰም "**ጠለሰመ**" ስር ተመ.

***ጠመለመለ**

ጥምልምል ቅ አቅም ወይም ጥንካሬ የሌለው።

ተጥመለመለ ግ 1. ሽባ፥ አቅመቢስ ሆነ። 2. ተጣጠፈ፥ ተጠቀለለ።

አጥመለመለ ግ 1. አዝለፈለፈ፥ አሽመደመደ፤ ሽባ፥አቅመቢስ አደረገ። 2. አጣጠፈ፥ ጠቀለለ።

ጠመመ ግ 1. ጎበጠ፥ ተወላገደ፥ ጋደድ አለ። 2. (ዘይ.) ክፉ፥ ፈቃደኛ አልሆን አለ፥ ክፉ አሰበ።

ጠማማ ቅ 1. ጎባጣ፥ ወልጋዳ፥ ገዳዳ። 2. (ዘይ.) ክፉ፥ ቅን ያልሆነ።

ጥመት ስ (ዘይ.) ክፋት፥ የጠባይ ወልጋዳነት።

ተጣመመ ግ ተወላገደ፥ ተንጋደደ፥ ጎበጠ።

አጣመመ ግ 1. አንጋደደ፥ አዘነበለ፥ አጎበጠ። 2 እንዳይሆን፥ እንዳይሳካ አደረገ (ጉዳይን)።

***ጠመረ**

ጣምራ ቅ ጥንድ፤ ሁለትነት ያለው።

ጣምራ ጦር ስ 1 መንታ ጫፍ ያለው ጦር። 2. እየተጋገዘ የሚዋጋ ሁለት የጦር ሃይል ።

ጥምር ቅ ጥንድ፥ የተጣመረ፥ የተባበረ።

ጥምር ቃል ስ ከአንድ በላይ በሆኑ ቃላት የተመሰረተ ቃል፤ ሃረግ።

ተጣመረ ግ አንድ ላይ ተደረገ፥ አንድ ሆነ፥ ተባበረ።

ተጣማሪ ስ 1. (ሰዋ.) አንድን ስም ለማጉላት በተደራቢ የሚገባ ቃል። *ሳበ ተማሪው ነገ ይመጣል* በሚለው ውስጥ "ተማሪው" ተጣማሪ ነው። ቅ 2. ተጫፋሪ ፥ ተጓዳኝ፥ አብር።

አጣመረ ግ አንድ ላይ አደረገ።

አጣማሪ ቅ ቀንጃ፥ ጓደኛ።

ጠመሰሰ ግ ጣሰ፤ ገለጠ (ደንን፥ ዳዋን)።

ጠመቀ^{1} ግ 1. ከተለያዩ የእህል አይነት ጠላን ወይም ቢራን አዘጋጀ። 2. ጨመቀ፥ ጠመዘዘ (እርጥብ ልብስን)። 3. አጣራ፤ ደህናውን ከአተላ ወይም ካአሰር ለየ።

ጠመቀ^{2} ግ በውሃ ወይም በፀበል ነከረ፥ ዘፈቀ።

ምጥማቅ ስ የማጥመቂያ ቦታ ወይም ገንዳ።

ጥምቀት ስ (ክር.) 1. ክርስቶስ የተጠመቀበትን ቀን በማሰብ ጥር 11 ቀን የሚከበር በአል። 2. ክርስትና መነሳት፥ መጠመቅ።

ጥምቀተ ባህር ስ በጥምቀት ዋዜማ ታቦት ከቤተክርስቲያን ወጥቶ የሚያድርበትና የጥምቀት በአል የሚከበርበት ቦታ።

ተጠመቀ ግ 1. ክርስትና ተነሳ። 2. ፀበል ተረጨ፥ ተነከረ።

አጠመቀ ግ 1. በውሃ ወይም በፀበል ነከረ፥ ዘፈቀ። 2. ክርስቲያን አደረገ።

አጥማቂ ስ የሚያጠምቅ ካህን።

ጠመኔ ስ በጥቁር ሰሌዳ ላይ ለመፃፊያ የሚያገለግል፥ የተለያየ ቀለም ያለው፥ ከኖራ የሚሰራ የፅህፈት መሳሪያ፤ ቾክ።

ጠመንጃ (ጠበንጃ) ስ የተለያየ መጠንና አይነት ያለውና ጥይት የሚጎርስ፥ ለጦርነት ወይም ለጥበቃ ወይም ለአደን የሚጠቀሙበት የጦር መሳሪያ።



ጠመንጃ

ጠመንጃ አቀባበለ በጠመንጃ ውስጥ ያለውን ጥይት ወደ ቧንቧው አስገብቶ ለተኩስ አዘጋጀ።

ጠመንጃ አጎረሰ ጥይት በጠመንጃው ውስጥ አስገባ።

[የ]ጠመንጃ መፍቻ ስ ጫፉ ሾል ብሎ ጠፍጠፍ ያለና ብሎኖችን ለመግጠም ወይም ለመፍታት የሚያገለግል መሳሪያ።

የጠመንጃ ዘንግ ስ የጠመንጃን ውስጠኛ አካል (ቧንቧን) ለማፅዳት የሚያገለግል ቀጭን የብረት ዘንግ።

***ጠመዘመዘ**

ጠመዝማዛ ቅ ቀጥተኛ ያልሆነ፣ ዘወርዋራ (መንገድ፣...)።

ጥምዝምዝ አለ ግ ተጥመዘመዘ፣ ተጠማዘዘ።

ተጥመዘመዘ ግ 1. ቀጥተኛነት የሌለው ወይም ዘወርዋራ ሆነ። 2. ተሲቃየ፣ ተፍተለተለ፣ ታመመ (ሆድ)።

አጥመዘመዘ ግ 1. አመመ (ሆድን)። 2. አፍተለተለ፣ ጠማዘዘ።

ጠመዘዘ ግ 1. አጣመመ፣ ቆለመመ። 2. ጨመቀ፣ ጠመቀ (የረጠበ ልብስን)። 3. አዞረ፤ አቅጣጫ ቀየረ (ለምሳሌ የመኪናን)። 4.(ዘይ.) ሃሳብን፤ አቋምን ቀየረ ወይም አስቀየረ (በማግባባት፣...)።

ጥምዝ ቅ የተጠመዘዘ፣ ጥቅል።

ጥምዝ ወርቅ ስ እንደሽቦ ያለና የተጠቀለለ ወይም የተጠማጠመ የወርቅ ጌጥ።

ጠምዛዛ ስ 1. ቀጭን ሆኖ ጥንካሬ ያለው፣ በቀላሉ የማይሰበር 2. (ዘይ.) ችኮ፣ ግታራ (ሰው)።

ተጠመዘዘ ግ 1. ተጣመመ፤ ተቆለመመ። 2. አቅጣጫ ቀየረ።

ተጠማዘዘ ግ ተቆላመመ፤ ተጣመመ።

አጠማዘዘ ግ አቆላመመ፣ አጣመመ።

ጠመዝማዛ "*ጠመዘመዘ" ስር ተመ.

ጠመዥር (ጠመጅ) ስ ስንዴ የሚመስልና ገለባው በቀላሉ የሚላቀቅ የገብስ አይነት።

ጠመደ^{1} ግ 1. ቀንበርን በበሬዎች አንገት ላይ በማንቆ በማሰር ለእርሻ አዘጋጀ። 2. ጀመረ፣ ተያያዘ (ስራን)። 3. ክፉኛ ጠላ።

ጥማድ ቅ ጥንድ (በሬ)።

ተጠመደ ግ 1. ቀንበር ተጭኖበት ለእርሻ ተዘጋጀ (በሬው)። 2. በስራ ተያዘ ወይም አንድ ነገር በማድረግ ላይ ሆነ። *በጧት በስራ ተጠምዷል።* 3. ተጠላ፤ በክፉ ሁኔታ የሚተኮረበት ሆነ።

ተጣመደ ግ ክፉኛ ተጣላ፣ በነገር ተያያዘ።

አጣመደ ግ ክፉኛ አጣላ፣ በነገር አያያዘ። 2. አንድን በሬ ከሌላ በሬ ጋር አቀናጀ ወይም ጠመደ።

አጣማጅ ስ 1. አብሮ የሚጠመድ ቀንጃ በሬ። ቅ 2. አብሮ የሚሰራ፣ የሚሰማራ፣...የስራ ጓደኛ።

ጠመደ^{2} ግ መሳሪያን፣ ፈንጂን፣ ወጥመድን (እንዲፈነዳ፣እንዲይዝ፣...) አዘጋጅቶ አስቀመጠ።

ወጥመድ ስ 1. እንስሳትን ለመግደል ወይም ለመያዝ የሚያገለግል መሳሪያ።2. ሌላን ሰው ለመጉዳት፣ ለማስናከል፣... የተጠነሰሰ ሴራ፣ ተንኮል፣...።

ወጥመዱ ያዘለት ያሰበው ተንኮል ወይም ሸር ተሳካለት።

ወጥመድ ውስጥ ገባ 1. በመጥፎ ወይም በተወሳሰበ ነገር ውስጥ ገባ። 2. የተንኮል ወይም የሴራ ሰለባ ሆነ።

አጠመደ ግ 1. ወጥመድን እንዲይዝ፣ ፈንጅን እንዲፈነዳ አድርጎ አዘጋጅቶ አስቀመጠ። 2. አሳን ከባህር፣ ከወንዝ፣... በመረብ ወይም በመንጠቆ አወጣ ወይም ያዘ። 3. ሴራ፣ደባ አዘጋጀ።

ጠመጅ "ጠመዥርን"ን ተመ.

ጠመጠመ ግ 1.በራስ ማሰሪያ፣ በሻሽ፣... ራስን ሸፈነ ወይም አሰረ። 2. አንድን ነገር በሌላ ነገር ላይ እየደጋገመ በማዞር ጠቀለለ (ለምሳሌ ገመድን በእንጨት ላይ)። 3. ተንኮል፣ ሸር፣ ነገር ሰራ።*ነገር ጠመጠመበት።*

ጠምጣሚ ቅ 1. ካህን፣ ቄስ። 2. (ዘይ.) ነገረ ሰሪ።

ጥምጣም ስ የ "ጥምጥም"ን 1ኛ ፍቺ ተመ.

ጥምጥም ስ 1. በራስ ላይ የተደገለለ፣ የታሰረ ሻሽ። ቅ 2. የተጠመጠመ፣ ጠመዝማዛ የሆነ(መንገድ፣ ነገር፣...)።

ጥምጥም አለ ግ 1. ተጠመጠመ። 2. ሰውነቱ ዳበረ፣ ጎላ፣ ጠነከረ። *ጥምጥም ያለ ሰውነት።*

ተጠመጠመ ግ 1. በአንድ ነገር ላይ በተደጋጋሚ በመዞር ተጠቀለለ፤ ተተበተበ። 2. አንቆ፣ እቅፍ አድርጎ ያዘ።

ጠማ

ጠማ አለ ግ 1. በሰለ፣ ጎመራ (እሸት)። 2. መጠጥ አለ።

ጠማ ግ 1. አሰኘ፣ አስፈለገ፣ አማረ (መጠጥ፣ ውሃ)። 2. (ዘይ.) ፈለገ፣ አሰኘው። *ትምህርት ጠምቶታል።*

ጥማት(ጥም) ስ (የውሃ፤ የመጠጥ፤ የእውቀት) ፍላጎት።

ጥም ቆረጠ አረካ፥ አጠገበ (መጠጥ)።

ተጠማ ግ 1. መጠጣት አሰኘው (ውሃን)። 2. (ዘይ.) አስፈለገ፥ ፈለገ፥ (እውቀት፥ ትምህርት)።

አስጠማ ግ የውሃ ጥም አሳደረ፥ አስከተለ።

ጠማማ "ጠመመ" ስር ተመ.

ጠምበለል "ጠንበለል"ን ተመ.

ጠምጣሚ "ጠመጠመ" ስር ተመ.

ጠሞረ ግ የተለያየ ቀለማት ያላቸውን ክሮች አንድ ላይ በማድረግ ሸረበ።

ጥሙር ቅ የተጠሞረ፥ የተሸረበ (ጥለት፥ ክር)።

ተጠሞረ ግ የተለያየ ቀለም ያለው ክር በአንድ ላይ ተሸረበ።

ጠሚጋ ቅ ክሲታ።

ጠረመሰ ግ 1. ሰረጎደ። 2. ሰበረ፥ ሸረፈ። 3. አስተኛ፥ ማሰ (ለምሳሌ አጥርን)።

ተጠረመሰ ግ 1. ተሰረጎደ። 2. ተሰበረ፥ ተሸረፈ። 3. ተኛ፥ ወደቀ (ለምሳሌ አጥር)።

ጠረረ ግ የፀሃይ ሙቀት ጋለ፥ ጠራራ ሆነ።

ጠራራ(ፀሃይ) ቅ የእኩለ ቀን ሃይለኛ የፀሃይ ሙቀት ። *በጠራራ ፀሃይ ወዴት ትሄዳለህ?*

ጠረሰ ግ 1. ዶለዶመ፥ ደነዘ፥ አልቆርጥ አለ (በለት)። 2. አላኘክ አለ፥ የሚሰቀጥጥ ስሜት ፈጠረ (ጥርስ)።

ተጣረሰ ግ 1. እርስ በእርስ ተደባደበ። 2.እርስ በርሱ ተፋጨ፥ ተጋጨ (ለምሳሌ ጥርስ)።3. ተቃወሰ፥ ተበላሸ (ክርክር፥ የነገር ስልት)።

አጣረሰ (አንጣረሰ) ግ 1. አማታ፥ አደባደበ። 2. አቃወሰ፥ አፋለሰ፥ አበላሸ (ክርክርን፥ የነገር ስልትን) ።

ጠረሰመ ግ ጠረመሰ፤ሰበረ፤ አደቀቀ።

ጠረቀ ግ 1. ጠረነቀ፥ አጥብቆ አሰረ። 2. ቸነከረ። 3. (ዘይ.) ብዙ አወራ፥ አወጋ። *ለግፋን ለንፈራጠ ወሬውን ሊጠርቅ ቀለ።* 4. (ዘይ.) እስኪጠግብ በላ።

ጠርቅ ቅ (ዘይ.) ብዙ የሚበላ፥ ሆዳም።

ተጠረቀ ግ ተጠረነቀ፥ ጠብቆ ታሰረ።

ጠረቀመ ግ 1.ወጋ፥ ሰካ። *እሾህ ጠረቀመብኝ።* 2. አጥብቆ አሰረ። 3. ዝም አሰኘ። 4. አጥብቆ ዘጋ ፥ ቆለፈ። 5. በጥፊ መታ፥ አጠናፈረ። *በጥፊ ጠረቀመብኝ።*

ተጠረቀመ ግ ተሰካ፥ ገባ። *እሾህ ተጠረቀመብኝ።* 2. ዝም አለ። 3. ተዘጋ፥ ተቆለፈ።

*ጠረቀመ

ጥርቃሞ ቅ 1. ከየትም ከየትም የተሰበሰበ። 2. ፋይዳ ቢስ፥ እርባና የለሽ።

ጥርቅም ቅ የተጠራቀመ፥ ከተለያየ ቦታ የተሰበሰበ፥ ስብስብ።

ጥርቅምቅም ቅ ከየቦታው የተሰበሰበ፥ ግሳንግስ።

ተጠራቀመ ግ 1. ተከማቸ፥ ተሰበሰበ። 2.ቀስ በቀስ ብዙ ሆነ።

አጠራቀመ ግ 1. አከማቸ፥ሰበሰበ፥ አስቀመጠ (ለምሳሌ ገንዘብን)። 2. አንድ ላይ አስቀመጠ።

ጠረቃ ግ ዳበረ፥ ወፈረ (ሰውነቱ)።

አጠረቃ ግ አዳበረ፥ አወፈረ።

ጠረቆሸ ግ ሸነቆረ፥ ቀደደ።

ጠረበ ግ 1. በመጥረቢያ፥ በመሮ፥...እየታገዘ አስተካከለ፥የሚፈለገውን ቅርፅ እንዲይዝ አደረገ (እንጨትን፥ ድንጋይን)። 2. (ዘይ.) ነቀፈ፥ ተቸ፥ ወረፈ(ሰውን)። *በሰላ ሂስ ጠረበው።*

መጥረቢያ ስ የእንጨት መቁረጫ ወይም መፍለጫ ምሳር።

መጥረቢያ

ጠራቢ ቅ ድንጋይን፥ እንጨትን በመጥረብ ወይም በመቆርቆር፥... ቅርፃ ቅርፅ የሚያወጣ (ሰው)።

ጠርብ ስ ለቤት ወይም ለአጥር፥ መስሪያ የሚያገለግል ረጅም ፍልጥ።

ጠርብ ያህላል ረጅምና ወፍራም ነው።

ጥራቢ ቅ ድንጋይ፥ እንጨት፥... ሲጠረብ የሚወድቅ ስብርባሪ፥ ድቃቂ፥ ፍቅፋቂ።

ጥርብ ቅ የተጠረበ ወይም የተስተካከለ (ድንጋይ፥ እንጨት)።

*ጠረበበ

ተንጠረበበ ግ 1. ተንደረበበ፥ ጢም ያለ ሆነ እስከ አፉ ሞላ (ሰፍር)። 2. አኮረፈ። 3.ተንጠረዘዘ፥ ዝናብ ሊጥል ደረሰ (ደመና)።

አንጠረበበ ግ በጣምሳይሞላ በድርበቡ ሰፈረ።

ጠረነቀ ግ 1. አጥብቆ አሰረ፥ ቀፈደደ። 2. መታ፥ ጠሰቀ።

ጠረን ስ የአካል ወይም የሰውነት ሽታ።

ጠረንገሎ(ጠረንገላ) ቅ ወደል፥ ጠብደል።

*ጠረወዘ

ጠርዋዛ ቅ ከልዋሳ፥ ገልዋዳ።

ጥርውዝ ጥርውዝ አለ ግ ወዲያ ወዲህ ተንከላወሰ፥ ተንገላወደ።

ተንጠራወዘ ግ ተንከላወሰ፥ ተንገላወደ።

አንጠራወዘ ግ አንከላወሰ፥ አንገላወደ።

ጠረዘ ግ 1. የተጻፈባቸውን ወይም ያልተጻፈባቸውን ብትን ወረቀቶች ወይም የብራና ቅጠሎች በመፅሃፍ መልክ አዘጋጀ (ወረቀቶቹን ወይም የብራና ቅጠሎቹን ላንድነት በመስፋት፥ በማጣበቅ፥...)። 2. ያረጀ ወይም ጥራዙ የተጎጠለ መፅሃፍን እንደገና አደሰ፥ ደጎሰ። 3. አሰረ፥ ጠፈረ(ለምሳሌ የተበታተኑ እቃዎችን አንድነት በማድረግ)። 4. ለጎመ (እንደ ላገልግል፥ ቁና፥.. ያለ የሰፌት እቃን)። 5. መታ፥ ጠረቀመ።

ጠራዥ ስ የጥራዝ ስራ ባለሙያ።

ጠርዝ ስ የአንድ አካል ጫፍ፥ ዳር።

ጠርዝ አስያዘ ስርአት፥ መስመር አስያዘ (ነገሩን)።

ጥራዝ ስ 1. የመፅሃፍ ቅርፅ (በአንድ ላይ የተያያዘ ወይም የተሰፋ ብራና ወይም ወረቀት)። 2. ብትን ወረቀቱ ወይም ብራናው የተያያዘበት ስፌት።

ጥራዝ ነጠቅ ቅ 1. ስለአንድ የእውቀት ዘርፍ ጠለቅ ያለ ትምህርት ሳይኖረው ወይም በደንብ ሳያውቅ ወይም ሳይማር በሚገባ እንደተማረና እንደሚያውቅ ሆኖ የሚያወራ። 2. (ዘይ.) ያልተረጋገጠ፥ ተባራሪ (ወሬ)።

ጥርዝ ሰውነቱ ድድር ያለ አጭር ሰው።

ተጠረዘ ግ ታሰረ፥ ተተበተበ፥ ተጠፈረ፥ ተሸፈነ።

***ጠረዘዘ**

ጠርዛዛ(ጠረዘዝ) ቅ 1. ሆደ ቀብዳዳ፥ ቆርጣጣ። 2. (ዘይ.) ቀብራራ፥ ኩሩ።

ተንጠረዘዘ ግ 1. ተንቀበደደ፥ ተንዘረጠጠ። 2. (ዘይ.) ኩራ፥ ተንቀባረረ።

አንጠረዘዘ ግ 1.አንቀበደደ፥ አንዘረጠጠ።

ጠረገ ግ 1. አፀዳ፥ ወለወለ፥ አጠራ። 2. አጨደ፥ ከስሩ ቆረጠ። 3. ሟጠጠ፥ ጨርሶ ወሰደ። 4. ጨረሰ፥ ገደለ። *ተላላፊ በሽታ ንብቶ ጠረጋቸው።* 5. ጨርሶ፥ ሟጦ በላ።6. በሃይል መታ (በዱላ)።

መጥረጊያ ስ እጀታ እንዲኖረው ተደርጎ ከሰሌን ወይም ከናይለን ከር ወይም ከቃጫ፥... የሚሰራና ለቤት ማፅጃነት የሚያገለግል መሳሪያ።

ጠራጊ ስ ቤት ወይም መንገድ የሚያፀዳ።

ጥራጊ ስ 1. አስፈላጊ ባለመሆኑ ከተለያዩ ቦታዎች (ከቤት፥ ከግቢ፥...) ላይ እየተጠረገ እንዲወገድ የሚደረግ ቆሻሻ።2.በድስት ወይም በሰሃን ውስጥ የቀረ ሙጣጭ ወጥ ወይም የምግብ ፍርፋሪ። 3. (ዘይ.፥ስድብ) የማይረባ፥ ምናምንቴ (ሰው)።

ጥርጊያ ስ 1. የተጠረገ፥ አባጣ ጎባጣው የተስተካከለ፥ የተደለደለ ሰፊ መንገድ፥ ጎዳና። 2. አንድ ነገር ለመስራት ወይም ለማከናወን አቅጣጫ የማስያዝ ጅማሮ።

ጥርግ አለ ግ 1. እብስ፥ ጭልጥ ብሎ ሄደ።2.ሙልጭ ብሎ ሄደ።

ተጠረገ ግ እብስ ብሎ ሄደ። *ተጠርጎ ሄደ።*

ተጠራረገ ግ ተያይዞ ሄደ።*ተጠራርገው ሄዱ።*

ጠረጠረ^{1} ግ 1. አንድ ነገር ሊሆን ወይም ላይሆን ይችላል ብሎ አሰበ፥ ሰጋ፥ፈራ።2. እምነት አጣ ወይም ሳይተማመን ቀረ።

ጠርጣሪ ቅ 1. ሊሆን ወይም ላይሆን ይችላል ብሎ የሚያስብ፥ የሚገምት። 2. ጎበዝ፥ ንቁ።

ጠርጣራ ቅ ንቁ፥ ጠንቃቃ።

ጥርጣሬ ስ አንድን ነገር እምኖ አለመቀበል፥ ማመንታት፥ መስጋት፥ መወላወል።

ጥርጥር ስ 1. እርግጠኛ ያለመሆን ሁኔታ። 2. ስጋት፥ እምነት ማጣት።

ጥርጥር የለውም እርግጥ ነው።

ተጠረጠረ ግ አንድ ነገር አድርጓል ወይም ፈፅሟል ተብሎ ታሰበ፥ ተገመተ፥ ታማ።

ተጠርጣሪ ቅ አንድን ወንጀል ፈፅሟል ተብሎ የሚገመት።

አይጠረጠርም 1. እርግጥ ነው። *ፈተናውን እንደሚያልፈው አይጠረጠርም።* 2. እምነት የሚጣልበት ወይም ታማኝ ነው።

ተጠራጠረ ግ 1. ሰጋ፥ ፈራ፥ ይሆናል ወይም ላይሆን ይሆናል ብሎ አሰበ። 2. አመነታ፥ አወላወለ፥ እምነት አጣ።

ተጠራጣሪ ቅ 1. እምነት የሌለው። 2. ሊሆን ወይም ላይሆን ይችላል ብሎ የሚያስብ።

አጠራጠረ ግ እውነተኛ ወይም እርግጠኛ መሆኑ አጠያያቂ ሆነ።

አጠራጣሪ ቅ ሙሉ በሙሉ የማይታመንበት፥ አጠያያቂ።

ጠረጠረ^{2} ግ 1. ፈለፈለ፥ሽፋኑን ወይም ገለፈቱን አነሳ (የባቄላን፥ የሽንብራን፥...)። 2. እየፈለፈለ በላ (የባቄላን አሹቅ ወይም እሸት፥...)።

ጥርጣሪ ስ የሽንብራ ወይም የባቄላ ፍሬ ሽፋን፥ ገለባ፥...።

ተንጠረጠረ ግ 1. ተንቀረቀበ፥ የሚፈለገው ከማይፈለገው እንዲለይ ተደረገ(ለምሳሌ እንክርዳዱ ከስንዴ)። 2. በብርድ፥ በድንጋጤ ምክንያት ሰውነቱ ተንቀጠቀጠ።

አንጠረጠረ ግ 1. አንቀረቀበ፥ ፍሬውን ከገለባ ለየ። 2. አንቀጠቀጠ፥ አንዘፈዘፈ (ብርድ፥ ድንጋጤ)። 3. (ዘይ.) አብጠረጠረ፥ በዝርዝር ተነተነ። *አንጠርጥሮ ያውቃል።*

እንጥርጣሪ ስ ብጣሪ፥ እንቅጥቃጭ።

ጠረጠሰ ግ 1. ደለደመ፥ ደነዘ። 2. (ዘይ.) አረጀ፥ ጨረጨሰ።

ጠርጣሳ ቅ 1. የደለደመ፥ የደነዘ። 2. (ዘይ.) ያረጀ፥ የጨረጨሰ።

ጥርጥስ ቅ ችርችፍ፡ ሰለት አልባ።

ጠረጴዛ ስ ላዩ ጠፍጣፋና ክብ ወይም ባለአራት ማእዘን የሆነ፥ በአብዛኛው አራት ወይም ሶስት እግር ያለው፥ ከእንጨት ወይም ከብረት፥... የሚሰራና ለእቃ ማስቀመጫ ወይም ለመመገቢያ፥ ለመፃፊያ፥...የሚያገለግል የቤት ቁሳቁስ።

በጠረጴዛ ዙሪያ በውይይት፥ በድርድር። *ልዩነትን በጠረጴዛ ዙሪያ መፍታት ስልጣኔ ነው።*

የጠረጴዛ ልብስ ስ ለጠረጴዛ እንደሽፋንና እንደጌጥ ሆኖ የሚያገለግል ጨርቅ ወይም ፕላስቲክ።

የጠረጴዛ ሰአት ስ በጠረጴዛ ላይ የሚቀመጥ ተለቅ ያለ ሰአት።

የጠረጴዛ ኪስ ስ የጠረጴዛ አካል ሆኖ ከጠረጴዛው ጋር አብሮ የሚሰራ የእቃ ማስቀመጫ ክፍል፤ መሳቢያ።

የጠረጴዛ ኳስ ስ ሁለት ሁለት ወይም አንዳንድ ሰው የያዙ ሁለት ቡድኖች መረብ አግድም መሃሉ ላይ በተወጠረበት ጠረጴዛ ላይ ለዚሁ የተሰራ ኳስን በራኬት እየመቱ ኳሷን በተቃራኒ ቡድን ክልል ላይ ለማሳረፍ የሚደረግ የውድድር ጨዋታ። ጨዋታው የሚካሄድበትም ኳስ በዚሁ ስም ይጠራል።

ጠረፈ ግ አሰረ፥ ቀረቀበ፥ ጠፈረ።

ጠረፍ ስ 1. ወሰን፥ ድንበር። 2. ዳር አገር።

ጠረፍ ጠባቂ ስ የሃገርን ዳር ድንበር የሚጠብቅ ወይም የሚያስከብር ወታደር።

ጠራ^1 ግ 1. እከሌ በማለትና ስምን በመጥቀስ ድምፅ አሰማ፥ ተናገረ። 2. ተናጋሪው ወዳለበት እንዲመጣ አደረገ ወይም ጠየቀ ወይም ና ወደ እኔ አለ። 3.ሰየመ፥ ስም አወጣ። 4. እንዲመጣ ወይም እንዲካፈል ጋበዘ፥ ጠየቀ (ለግብዣ፥ ለስብሰባ፥...)። 5. አቃጨለ፥ የደወል ድምፅ አሰማ። *ስልኩ እየጠራ ነው።*

መጥሪያ ስ 1. ከፍርድ ቤት ወይም ከፖሊስ ጣቢያ ወይም ከቀበሌ፥.. ተከሳሽን ወይም ምስክርን ለማቅረብ ወይም ለመጥራት የሚሰጥ ደብዳቤ። 2. ሲጫኑት ድምፅ የሚያሰማ ወይም የሚደወልና ለጥሪ የሚያገለግል ደወል።

ጥሪ ስ 1. ስምን በመጥቀስ መጥራት። 2. በአንድ አይነት ጉዳይ ወይም ስነስርአት ላይ በመገኘት የጉዳዩ ተካፋይ ወይም ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚጠይቅ መልእክት ወይም ግብዣ።

የጥሪ ወረቀት ስ (ለግብዣ፥ ለስብሰባ፥...) እንዲመጡ ወይም እንዲሳተፉ ለማድረግ የሚሰጥ የግብዣ ወረቀት ወይም ደብዳቤ።

ተጠራ ግ 1. ተናጋሪው ወዳለበት ወይም መልእክቱን ወደአስተላለፈው ዘንድ እንዲሄድ ተነገረው። 2. ስም ወጣለት፥ ተሰየመ፥ ተባለ። *ከተማው ሐዋሳ [illegible] ተብሎ ተጠራ።* 3. እንዲመጣ ወይም እንዲካፈል ተጋበዘ።

ተጠሪ ስ ወኪል፥ እንደራሴ።

ተጣራ ግ ጮክ ብሉ ስምን ጠራ ወይም እገሌ አለ።

ተጠራራ ግ አንዱ ሌላውን እየጠራ ተሰባሰበ።

አስጠራ ግ ስምን በጥሩ ወይም በመጥፎ ነገር አስነሳ።

ጠራ^2 ግ 1. ፀዳ፥ ንፁህ ሆነ። 2. ጠለለ፥ የተጣራ ሆነ። 3. ወለል አለ፥ ደመና የሌለው ሆነ (ሰማይ)።

ጥሩ ቅ 1. ንፁህ፥ የተጣራ። 2. ደህና፥ ቆንጆ፥ ጥራት ያለው። 3. መልካም፥ ማለፊያ። 4. እሺ፥ ይሁን ለማለት የሚያገለግል ቃል።

ጥራት ስ ጥሩነት፥ ብቃት (የእህል፥ የስራ፥ የእቃ፥...)።

ተጣራ ግ 1. ንፁህ ሆነ፥ ጠራ። 2. ተረጋገጠ፥ እውነቱ ታወቀ (ነገር)።3.ተሸጠ፥ አለቀ (ሸቀጥ፥...)። 3. ልቅም ተደርጎ ተሰራ(ተዝረክርኮ የነበረው)።

አጠራ ግ 1. አፀዳ፥ ንፁህ አደረገ። 2.አጠለለ፥ አጣራ። 3.ሳያዝረከርክ ልቅም አድርጎ ሰራ(ተዝረክርኮ የነበረውን)።

አጣሪ ስ ችርቻሪ ነጋዴ (ልዩ ልዩ ሸቀጦችን)።

አጣራ ግ 1. መጠጥን ከተጠመቀበት ወይም ከተጣለበት ወደ ሌላ እቃ እያጠለለ ገለበጠ። 2. አረጋገጠ፥ እውነቱን አወቀ። 3. ጨርሶ ሸጠ(ሸቀጣ ሸቀጥን፥...)። 4. ልቅም አድርጎ ሰራ።

ማጣሪያ ስ 1. ማጥለያ፥ ወንፊት። 2. (ስፖ.) ለመጨረሻ ውድድር የሚቀርቡ ተወዳዳሪዎችን ለመለየት የሚደረግ ውድድር።

[የ] ማጣሪያ ሽያጭ ስ የነበረውን ሸቀጥ በሙሉ በሌላ ለመተካት ወይም የንግድ ዘርፉን ለመለወጥ፥... ሲፈለግ እቃዎቹን ከመደበኛ ዋጋቸው በመቀነስ የሚካሄድ ሽያጭ።

ጠራራ "**ጠረረ**" ስር ተመ.

*ጠራራ

ተንጠራራ ግ ቁመቱ የማይደርስበት ቦታ ለመድረስ እጁን ዘረጋ። 2. ሰውነቱን በመለጠጥ ወይም በመዘረጋጋት አፍታታ። 3. ተኩራራ፥ ያልሆነውን ለመሆን ሞከረ።

አንጠራራ ግ 1. እጅና እግሩን በሃይል በመዘርጋት ለማስረዘም ሞከረ (አንድ ነገር ለመንካት ወይም አንድ ነገር ላይ ለመድረስ)።

2. አኩራራ።

ጠራቢ "ጠረበ" ስር ተመ.

***ጠራወዘ**

ጠርዋዛ ቅ ክልዋላ።

ጥርውዝ ጥርውዝ አለ ግ ወዲያ ወዲህ ተንከላወሰ።

ተንጠራወዘ ግ ተንከላወሰ።

አንጠራወዘ ግ አንከላወሰ።

ጠራዥ "ጠረዘ" ስር ተመ.

ጠራጊ "ጠረገ" ስር ተመ.

ጠር " *ፀረረ" ስር "ፀር" ን ተመ.

ጠርሙስ ስ ከመስታወት መሳይ ነገር የሚሰራ ከአፉና ከአንገቱ ጠባብ የሆነ የፈሳሽ መያዣ።

ጠርቅ "ጠረቀ" ስር ተመ.

ጠርቡሽ ስ በራስ ላይ የሚደረግ የቆብ አይነት።

ጠርብ "ጠረበ" ስር ተመ.

ጠርዋዛ "*ጠረወዘ" ስር ተመ.

ጠርዛዛ "*ጠረዘዘ"ስር ተመ.

ጠርዝ "ጠረዘ" ስር ተመ.

ጠርጣሪ "ጠረጠረ[1] "ስር ተመ.

ጠርጣራ ዝ.ከ.

ጠርጣሳ "ጠረጠሰ" ስር ተመ.

ጠሮ

ጠሮ ሃረግ ስ ቀፎና ቅርጫት የሚሰራበት ጠንካራ የሆነ የሃረግ አይነት።

ጠሮ ነፍስ ስ ሃይለኛ አውሎ ነፋስ።

ጠሰቀ ግ 1. አጥብቆ አሰረ፤ ቀፈደደ። 2. በብዛት በላ። 3. አመቀ፤ ጠቀጠቀ። 4. ነረተ ፤ ደሰቀ።

ጥሰቅ ቅ የሞላ።

ጥስቅ ያለ ሰውነት ስ ሙሉ ሰውነት።

ጥስቅ አደረገ ግ 1. ቀስፎ ያዘ፤ አላስተነፍስ አለ (ህመም)። 2. ጠሰቀ።

ጥስቅ አድርጎ በላ በደንብ አድርጎ በላ።

ጠሰጠሰ ግ 1. ነቀዘ፤ ጠነጠነ (እንጨት)። 2. (ዘይ.) አረጀ፤ ጨረጨሰ።

ጠስጣሳ ቅ ያረጀ፤ የጨረጨሰ።

ጠቀለለ ግ 1. ሸበለለ፤ ጠመጠመ። 2. ሰበሰበ፤ አንድ አድርጎ ያዘ። 3. መትቶ ጣለ። 4. ህጋዊ ባልሆነ ግንኙነት የደፈራትን ልጃገረድ ወይም ያስረገዛትን ሴት አገባ። 5. ጨመረ፤ አካተተ። *ማህበራችን ወጣቶችንም ይጠቀልላል።* 6. የጋራ የነበረን ነገር ለብቻው ወይም ለግሉ አደረገ።

መጠቅለያ ስ ሴቶች ፀጉራቸውን የሚጠቀለሉበት ከፕላስቲክ ወይም ከብረት የተሰራ እቃ፤ ቢጎዲን።

ጠቅላላ ተው.ግ. ሁሉም፤ በሙሉ። ቅ 2. ሁሉንም የሚይዝ ወይም የሚያካትት። *ጠቅላላ ሪፖርት።*

በጠቅላላ ተው.ግ. 1. በሙሉ። 2. ሙሉ በሙሉ በአንድነት፤ በአጠቃላይ፤ በድምሩ።

ጠቅላላ ምርጫ ስ 1. ሁሉም አባላት የተሳተፉበት ምርጫ። 2. አጠቃላይ የአመራር አባላትን ለመምረጥ የሚካሄድ ምርጫ።

ጠቅላላ ውጤት ስ የተገኘው ሁሉም ውጤት በድምሩ።

ጠቅላላ ገቢ ስ የተገኘው ሁሉም ገቢ በድምሩ።

ጠቅላላ ጉባኤ ስ ሁሉንም አባላት የሚያጠቃልል ወይም የሚወክል ስብሰባ ወይም ጉባኤ።

ጠቅላይ ቅ 1. የበላይ፤ ከፍተኛ። 2. በስሩ የተለያዩ ነገሮችን፤ ክፍሎችን የሚያካትት።

ጠቅላይ ሚኒስትር ስ የአንድን ሃገር መንግስት ወይም መስተዳድር የሚመራ የሚኒስትሮች ሰብሳቢ።

ጠቅላይ ግዛት ስ ክፍለ ሃገር (ከ1966 ዓ.ም. በፊት ይባል የነበረ)።

ጥቅል ቅ 1. የተጠቀለለ፤ ሽብልል። ስ 2. በወፍራሙ የተቦካ ሊጥ። 3. ድምር። 4. በአንድነት የተጠቀለለ ወይም የታሰረ ነገር፤ እቃ፤ እስር።

የጥቅል ስም ስ (ሰዋ.) ብዙ ነገሮች በአንድነት ተጠቃለው የሚጠሩበት ስም(ለምሳሌ መንጋ፤ እፅዋት)።

ጥቅል ጎመን ስ ቅጠሉ በአንድነት እየተጠቀለለና እየተነባበረ የሚበቅል፤ መልኩ ነጣ የሚልና ቅርፁ ድቡልቡል የሆነ የጎመን አይነት።

ጥቅል ጎመን

ተጠቃለለ ግ 1.ተፈፀመ፤ተከናወነ፤አለቀ። *ሴሚናሩ ተጠቃለለ።* 2. አንድ ላይ ተደመረ፤ ተካተተ።

አጠቃለለ ግ 1. አንድ ላይ አደረገ፤ አካተተ። 2.ደመደመ (ንግግርን፤...)።3.የግሉ ወይም የብቻው አደረገ።

ማጠቃለያ ስ 1. ማሳረጊያ፤ ማብቂያ፤ መጨረሻ። 2. መደምደሚያ።

አጠቃላይ ቅ 1. ሁሉንም አካቶ የሚይዝ ወይም የሚያሳትፍ። 2. ሁሉንም የሚመለከት፤ የሚያቅፍ፤...። 3.ዝርዝር ያልሆነ።

በአጠቃላይ ተው.ግ. 1. በድምሩ፤ በሙሉ።

2. በጥቅሉ፣ ባጭሩ (ቀደም ሲል የተገለፀው ወይም የተዘረዘረው ነገር ሲጠመቅ ወይም በአንድነት ሲሰበሰብ)።

ጠቀመ^1 ግ 1. ረዳ፣ አገለገለ፣ በጀ። 2. ቢቃ፣ አጠገበ።

ጠቃሚ ቅ ጥሩ፣ ተፈላጊ፣ የሚያገለግል።

ጥቅም(ጠቀሜታ) ስ 1. እርባና፣ ፋይዳ፣ ረብ። 2. አገልግሎት። 3. ትርፍ ወይም ውጤት።

ከጥቅም ውጪ ሆነ ተበላሸ፣ ከብልሽት የተነሳ አገልግሎት የማይሰጥ ሆነ።

ከጥቅም ውጪ አደረገ አበላሸ፣ አሰናከለ።

ጥቅም አሳዳጅ ለግል ጥቅሙ የሚሯሯጥ።

ጥቅም የለውም 1. ምንም አያገለግልም።2. ትርፍ የለውም።

ተጠቀመ ግ 1. ተገለገለ።*ረቂቁን ለመጻፍ እርሳስ ተጠቅመናል።* 2. ረብ፣ ፋይዳ፣ ትርፍ አገኘ።

ተጠቃሚ ቅ 1. ተገልጋይ። 2. ረብ፣ ፋይዳ፣ ትርፍ የሚያገኝ።

ተጠቃቀመ ግ ተረዳዳ፣ ተጋገዘ (አንዱ ሌላውን በመጥቀም)።

አጠቃቀም ስ 1. በአንድ ነገር ወይም መሳሪያ ለመገልገል የሚያስችል እውቀት፣ ችሎታ (የአከፋፈት ፣ የአዘጋግ፣...)። 2. አንድ ነገር በአገልግሎት ላይ የሚውልበት መንገድ፣ ዘዴ፣ እውቀት። *የቃላት አጠቃቀም።*

ጠቀመ^2 ግ ሰፋ፣ ደረተ፣ ጣፈ።

ጠቀሜታ "ጠቀመ^1 ስር "ጥቅም"ን ተመ.

ጠቀራ(ጠቀሮ) ስ ጥላሸት፣ ጥቀርሻ።

ጠቀራም ቅ ጥቀርሻ የለበሰ፣ የጠቀረ።

ጠቀሰ^1 ግ 1. ጠራ፣ አመለከተ (በእጅ፣በአይን)። 2. ለመረጃ ወይም ለምስክርነት ከንግግር፣ ከፅሑፍ፣... ያገኘውን እንዳለ ቀድቶ ወይም ወስዶ በቃል ወይም በፅሑፍ አቀረበ (ምንጩን ጠቀሰ)።

ጥቅስ ስ 1. ለመረጃነት፣ ለምስክርነት፣... ከአንድ መፅሃፍ ወይም ንግግር ውስጥ የተወሰደ ፅሑፍ፣ አባባል።

ጥቅሻ ስ በአይን ወይም በእጅ የሚደረግ ጥሪ ወይም ምልክት።

ጠቀስ አደረገ ግ በምልክት ወይም በጥቅሻ ጠራ ።

ተጠቃቀሰ ግ 1. በጥቅሻ መልእክት፣ ሃሳብ ተለዋወጠ። 2.ተጠራራ። *ሰዎቹ ሌቦቹን ከመካከላቸው ተጠቃቅሰው ሄዱ።*

ተጠቃቀሱበት በመጠቃቀስ አሾፉበት (አጠገባቸው ያለውን ሰው)።

ተጣቀሰ ግ ተመሳከተ፣ ተወራረሰ።

ጠቀሰ^2 ግ ነከረ (ወጥን በእንጀራ፣ ቀለምን በብርእ ፣...)።

አጠቀሰ ግ እንጀራን ወይም ዳቦን በወጥ፣ በተልባ፣... ነከረ (ለመብላት) ወይም ብርእን ቀለም ውስጥ ነክሮ አወጣ (ለመፃፍ)።

አጠቃቀሰ ግ እንጀራን ወይም ዳቦን ወጥ አስነካ (ለመብላት)።

ጠቀጠቀ ግ 1. አመቀ፣ አጠቀ። 2. ዘጋ፣ ወተፈ(ቀዳዳን)። 3. አፍንጫን አፈነ፣ አላስተነፍስ አለ(ጉንፋን)። 4. ረገጠ፣ ደቀደቀ፣ ረመረመ። 5. ዘርዛራ፣ሸክሻካ እንዳይሆን አደረገ (ወንፊትን፣ ወርቅን)። 6. ብዙ ቦታ በሳ (በሹል ነገር)። 7. አለፍ አለፍ እያለ ወጋ ወጋ አደረገ፣ አስጌጠ (ዳቦን፣ ቂጣን)። 8. (ዘይ.) አብዝቶ ጎረሰ፣በጣም እስኪጠግብ በላ። 9. (ዘይ.) ነካካ (በነገር)።

ጠቃጠቆ ቅ 1. የነጠብጣብ ምልክት፣ ዝንጉርጉር፣የተለያዩ ቀለማት ስብጥር። 2. አልፎ አልፎ የጠባሳ ምልክት ያለበት። *ፈንጣጣ ያበላሸው ፊቱ ጠቃጠቆ ሆኖ ቀረ።*

ጥቅጥቅ ቅ 1.ዘርዛራ ወይም ሸክሻካ ያልሆነ። (ወርቅ፣ ወንፊት።) 2. ተቀራርቦ የበቀለ፣ ጭፍግ ወይም ጭፍቅ ያለ (ለምሳሌ (ጫካ))።

ጥቅጥቅ ያለ ጨለማ ድፍን ያለ፣ እይታን ፈፅሞ የሚከለክል፣ ድቅድቅ ያለ ጨለማ።

ጥቅጥቅ አደረገ ግ ጠቀጠቀ።

ጥቅጥቅ አድርጎ ካደ ፈፅሞ ካደ ።

ተጠቀጠቀ ግ 1. ተዘጋ ፣ ተደፈነ (አፍንጫ)። 2. ዘርዛራ እንዳይሆን ተጠጋግቶ ተሰራ (ሹራብ፣ ወርቅ፣..)።

ጠቃ ግ ሰረረ፣ እንስቷ ላይ ወጣ፣ መታ(ለእንስሳት)።

ጠቅ አደረገ ግ ወጋ።

ተጠቃች ግ ተሰረረች (ጊደር)።

አስጠቃ ግ አሰረረ።

***ጠቃ**

ጥቃት ስ 1. በደል፣ ግፍ፣ ጭቆና። 2. የሃይል ርምጃ (የጦርነት)።

ጥቃተኛ ቅ ግፍ፣ በደል የተፈፀመበት።

ተጠቃ ግ 1. ግፍ፣ ጭቆና ደረሰበት፣ ተበደለ። 2. ሽንፈት ደረሰበት።

አጠቃ ግ 1. በደለ፣ ግፍ አደረሰ፣ ጨቆነ (ሰውን)። 2. በውድድር ወይም በጦርነት አሸነፈ፣ የበላይነትን ያዘ።

አጥቂ ስ 1. በደል፣ ግፍ፣ ጭቆና የሚያደርስ።2.(በውድድር፣በጦርነት፣...) የበላይነትን የያዘ ያየለው ወገን። 3. በእግር ኳስ

ጨዋታ ጊዜ በተቃራኒው ቡድን ላይ ግብ ለማስገባት በፊት ለፊት መስመር የሚጫወት ተጫዋች።

አስጠቃ ግ 1. በደል፣ ግፍ እንዲደርስ አደረገ ወይም መንገድ ከፈተ። 2. ጥቃት እንዲመጣ ምክንያት ሆነ።

ጠቃጠቀ "ጠቀጠቀ" ስር ተመ.

ጠቅላላ "ጠቀለለ" ስር ተመ.

ጠቅላይ ዝ.ከ.

ጠቆመ ግ 1. አመለከተ፣ አሳየ፣ ነገረ። 2. ነካ፣ ወጋ፣ ደነቀለ። 3. የሚያሳክክ የሰውነት ቆዳን በጣት ወይም በጥፍር ወጋ። 4. ለምርጫ፣ ለውድድር በእጩነት አቀረበ።

ጠቋሚ ስ 1. አመልካች፣ አንድን ሁኔታ የሚያሳይ። 2. የሚመራ፣ የሚያሳይ (አቅጣጫን)። 3. ሊመረጥ ወይም ሊወዳደር ይገባል ብሎ የሚያምንበትን ሰው በእጩነት የሚያቀርብ።

ጥቆማ ስ 1. በሚስጢር፣ በድብቅ መንገር። *ነገሩ በጥቆማ ተደርሶበታል።* 2. ለምርጫ ወይም ለውድድር እጩን የማቅረብ ሂደት።

ተጠቆመ ግ 1. በሚስጢር ተነገረ። 2. ለምርጫ ወይም ለውድድር ቀረበ።

ተጠቋሚ ስ ለምርጫ ወይም ለውድድር የቀረበ፣ እጩ።

ተጠቋቆመ ግ ተጠቃቀሰ።

ጠቆረ ግ 1. ከሰል ወይም ጥላሸት መሰለ። 2. ደመና ያዘ፣ ዝናብ አረገዘ (ሰማይ)። 3. ፊልሙ ላይ የተቀረፀው የፎቶግራፍ ምስል እንዲታይ ሆነ ወይም ተደረገ። 4. ከጉዳት፣ ከብስጭት፣ ከፀሃይ ሃሩር፣... የተነሳ መልኩ ጠየመ፣ ከሰል መሰለ።

ጠቋራ ቅ በጣም ጥቁር፣ ከሰል የመሰለ።

ጥቁራት ስ ንቅሳት፣ ውቅራት።

ጥቁሬ ዝንጀሮ ስ ጠቆር ያለ መልክ ያለው የዝንጀሮ አይነት።

ጥቁር (ብ.ቁ **ጥቋቁር**) ቅ 1. የከሰል መልክ ያለው። 2. የነጭ ቀለም ተቃራኒ፣ ከሰል ወይም ጥላሸት የመሰለ የቀለም አይነት። 3. ጠይም ወይም ጥቁር ቆዳ ያለው ህዝብ ዘር የሆነ (ሰው)።

ጥቁር ውሻ ውለድ (እር.) ጉድ ውለድ።

ጥቁር መጣፍጥ ስ ጥቁር አዝሙድ።

ጥቁር ምላስ ቅ እርግማኑ ይደርሳል ተብሎ የሚፈራ (ሰው)።

ጥቁር ራስ ስ ያልመነኮሰ፣ ቆብ ያልጫነ፣ አለማዊ የሆነ ሰው።

ጥቁር ሰሌዳ ስ በጠመኔ እየተፃፈበት ለማስተማሪያ እንዲያገለግል፣ ብዙውን ጊዜ ጥቁር ቀለም ተቀብቶ የተዘጋጀ ሰሌዳ።

ጥቁር ሰማይ ስ ደመና የሌለበት የጠራ ሰማይ።

ጥቁር ሰማያዊ ቅ 1. ደማቅ ጠቆር ያለ ሰማያዊ መልክ ያለው። ስ 2. ጠቆር ያለ ሰማያዊ ቀለም።

ጥቁር ስንዴ ስ ፍሬው ጠቆር የሚል የስንዴ አይነት።

ጥቁር አዝሙድ ስ ለዳቦ፣ ለወጥ ማጣፈጫ የሚያገለግል ፍሬው ጥቁር የሆነ ቅመም።

ጥቁር እንግዳ ስ 1. መጥቶ የማያውቅ፣ ከፍተኛ ክብርና መስተንግዶ የሚደረግለት ሰው። 2. የጉንዳን የምስጢር ስም።

ጥቁር እንጨት ስ ውስጡ ድፍንና በጣም ጠንካራ የሆነ የእንጨት አይነት፤ ዞጲ።

ጥቁር ደመና ስ በሰማይ ላይ ጨለማ መስሉ የሚታይ ዝናብ ያዘለ ደመና።

ጥቁር ድንጋይ ስ ጠንካራ የሆነ፣ በቀላሉ የማይሰበር፣የማይፈረካከስ የድንጋይ አይነት።

ጥቁር ገበያ ስ ህገወጥ የሆነ ግብይት፣ በተለይም የውጭ ምንዛሬ ልውውጥ።

ጥቁር ገብስ ስ ፍሬው ጠቆር የሚል የገብስ አይነት።

ጥቁር ጤፍ ስ ከሌላው ጤፍ ይልቅ በብረት ማእድን የበለፀገና፣ እንጀራው ሲጋገር ቡናማ መልክ የሚይዝ የጤፍ አይነት።

ተጠቆረ ግ 1. ተነቀሰ፣ ተወቀረ። 2. በእመድ ታሸ (ዘንጋዳ)።

አጠቆረ ግ 1. መልክን አጠየመ (ሃሩር፣...)። 2. በእመድ አሸ (ዘንጋዳን)። 3. በምርጫ ፈተና ጊዜ ከተሰጡት የመልስ ምርጫዎች መካከል፣ መልሱን በመምረጥ በተሰጠው ተራ ቁጥር ወይም ፊደል ስር ባለው የመልስ ቦታ ላይ ምልክት አደረገ፣ ቀባ። 4. ፎቶግራፍ በፊልም ላይ እንዲታይ አደረገ (ፊልሙን በተለያዩ የፎቶግራፍ ቅመሞች ውስጥ በመጨመር)።

አስጠቆረ ግ ፊልሙ ላይ ፎቶው ወይም ምስሉ እንዲታይ አደረገ።

ጠቋሚ "ጠቆመ" ስር ተመ.

ጠቋራ "ጠቆረ" ስር ተመ.

ጠበለተኛ "ፀበል" ስር "ፀበለተኛ"ን ተመ.

ጠበል "ፀበል"ን ተመ.

ጠበል ጣዲቅ "ፀበል" ስር "ፀበል ፀዲቅ"ን ተመ.

ጠበረረ ግ 1. በጣም ጋለ፣ ሰማ (ምጣድ)። 2. ሞቀ፣ ጠራራ ሆነ (ፀሃይ)። 3. ደረቀ፣ ተቃጠለ (ተክል፣ ቅጠል)።

አጠበረረ ግ 1. አጋለ፣ አሰማ (ምጣድን)። 2. አደረቀ።

*ጠበረረ

ጠብራራ (ጥብርር) ቅ ቀብራራ፣ ኩሩ፣ ጀግን።

ጥብርር አለ ግ ቅብርር አለ፣ ኮራ፣ ታበየ።

ተንጠባረረ ግ ኮራ፣ ተንቀባረረ፣ ተጀነነ።

አንጠባረረ ግ አንቀባረረ፣ አኮራ፣ ጀነነ።

*ጠበረበረ

ተጥበረበረ ግ ተብረቀረቀ፣ተብለጨለጨ፣ ተንፀባረቀ።

አጥበረበ (አጭበረበረ) ግ አንፀባረቀ፣ አብረቀረቀ፣አብለጨለጨ፣ አይን እንዳያይ አደረገ (ንፀብራቅ፣ ብልጭልጭታ)።

ጠበሰ ግ 1. ዘይት፣ ቅቤ፣... ጨምሮ በእሳት አንጨረጨረ፣ አበሰለ (ስጋን፣አትክልትን)። 2. ለበለበ፣አቃጠለ፣ተኮሰ።3.መታ (በጥይት፣ በአርጩሜ፣...)። 4. (ዘይ.) አቃጠለ፣ አናደደ፣ አሳረረ። *በነገር ጠበሰኝ።* 5. (ያራዳ አነ.) ሴትን አሽኮረመመ፣ አባበለ።

መጥበሻ ስ እጀታ ያለው ሆኖ ከብረት ወይም ከሸክላ የሚሰራና ለስጋ፣ ለድንች፣... መጥበሻነት የሚያገለግል እቃ።

ጠባሳ ቅ 1. በቃጠሎ፣ በቁስለት ምክንያት ሰውነቱ ላይ ምልክት ያለበት። ስ 2. በእሳት ተቃጥሎ ወይም በሌላ ምክንያት ቆስሎ ከዳነ በሗላ በሰውነት ላይ የሚቀረው ምልክት። 3. (ዘይ.) የመጥፎ ድርጊት አሻራ።

ጠባሳው የማይሽር የማይረሳ፣ ሁሌም የሚከነክን ።

ጥብስ ቅ 1. ያለ ውሃ በዘይት፣ በቅቤ ወይም በእሳት ብቻ የበሰለ (ምግብ)። ስ 2. በዘይት፣ በቅቤ ወይም በእሳት ብቻ የበሰለ ስጋ ።

ጥብስ ወጥ ስ ስጋው ለብቻ ከተጠበሰ በሗላ የሚሰራ ወጥ።

ተጠበሰ ግ ተቃጠለ፣ ተናደደ፣ አረረ (በነገር)።

ተጧበሰ ግ (ያራዳ አነ.) አንድ ነገር ለማግኘት፣ ለማከናወን፣ ጉዳይ ለማስፈፀም ታገለ፣ ተሯሯጠ ወይም በሌላ ሰው አማካይነት አለዚያም በራሱ ቅልጥፍና አንድን ጉዳይ ለማስፈፀም ቻለ።

ጠበሰቀ ግ መታ፣ ነረተ (በዱላ፣ በቡጢ)።

ጠበቀ^{1} ግ 1. አዋለ፣ አገደ (ከብትን)። 2.ተንከባከበ፣ እያየ፣ እየተከታተለ መጥፎ ነገር እንዳይመጣ ጥንቃቄ አደረገ፣ አደጋ እንዳይደርስ ተቆጣጠረ። 3.ቆየ። *ተራ እስከሚደርስህ ጠብቅ።* 4. አከበረ (ህግን፣ መብትን፣..)።

ጠባቂ ስ 1. አደጋ እንዳይደርስ ጥንቃቄ ወይም እንክብካቤ የሚያደርግ (በሰው፣ በንብረት ላይ)። 2. ከብት የሚያግድ፣ እረኛ።

ጥበቃ ስ ጉዳት ወይም አደጋ እንዳይደርስ ጥንቃቄ የማድረግ፣ የመከታተል ተግባር።

ጥበቃ ጓድ ስ የአንድን አካባቢ፣ ፀጥታ ወይም ስነ ስርአት ለማስከበር የተመደበ ሰው፣ ቡድን።

ጥብቅ ቅ እንዳታረግዝ የግብረስጋ ግንኙነት ከማድረግ የተቆጠበች (ሴት)።

ተጠበቀ ግ 1. በጥንቃቄ፣ በእንክብካቤ ተያዘ። 2. እንዳለ ሆነ፣ ፀና። 3. ተከበረ፣ ተግባራዊ ተደረገ (ህግ፣ ደንብ)። 4. ተከለከለ፣ተቆጠበ፣ ተወገደ፣ ተገለለ።*ከመጠጥ ተጠብቆ ይኖራል።*

አስጠበቀ ግ እንዲጠብቅ፣ እንዲከበር አደረገ። *መብቱን አስጠበቀ።*

ጠበቀ^{2} ግ ጠነከረ፣ ጠና፣ ከረረ፣ በቀላሉ የማይፈታ ሆነ።

የጠበቀ ሰላምታ የጋለ፣ ከፍ ያለ ሰላምታ።

የጠበቀ ግንኙነት የቀረበ ግንኙነት፣ ወዳጅነት።

ጠባቃ ቅ1. ጠንካራ፣ ልል ያልሆነ። 2. ጠባብ።

ጥብቅ ቅ 1. ጠንካራ፣ የከረረ፣ በቀላሉ የማይነቃነቅ፣ የማይፈታ። 2. ዋና፣ ብርቱ። *ለጥብቅ ጉዳይ ትፈለጋለህ/ ጥብቅ ማስጠንቀቂያ።* 3. የቅርብ፣ ታማኝ። *ለኔ ጥብቅ ወዳጄ ነው።* 4. ጠንቃቃ። 5. (ዘይ.)ንፉግ፣ ስስታም።

አጠበቀ ግ 1. አጠነከረ፣ እንዳይላላ፣ በቀላሉ እንዳይፈታ አደረገ። 2. አሉተው አለ፣ አከረረ (ሃዘንን፣ ነገርን)።

አጥባቂ ቅ ሁኔታዎችን በቀላሉ የማያይ፣ አክራሪ።

አጥብቆ ተው.ግ 1. በጣም። *ነገር አጥብቆ ይሸማል።* 2.አጠንክሮ፣ ደጋግሞ።*ስለሰውየው አጥብቆ ጠየቀኝ።*

ጠበቀ^{3} ግ 1. ቆየ። *እስኪመጣ ጠብቀው።*2. ሊሆን ወይም ላይሆን ይችላል ብሎ ገመተ፣ አሰበ (አንድ ነገር)። 3. አንድ ነገር እስከሚሆን ታግሶ ቆየ።

ተጠበቀ ግ ይሆናል ተብሎ ተገመተ። *የተጠበቀውን ያህል ውጤት አግኝተናል።*

ተጠባበቀ ግ 1. ጠበቀ። 2. ተከታተለ፣ በአይነ ቁራኛ ተመለከተ።

መጠባበቂያ ስ 1.ለችግር፣ ለአደጋ፣... ጊዜ የተቀመጠ ገንዘብ። 2. በጎደለ፣ በተበላሸ ነገር ፋንታ በምትኩ የሚገባ እቃ።

ተጠባባቂ ቅ 1. ምትክ፣ በጎደለው ፋንታ የሚተካ፣ የሚገባ። ስ 2. ሹመቱ ወይም የተሰጠው የሃላፊነት ቦታ ገና ያልፀደቀለት ወይም ለጊዜው ብቻ ሃላፊ ሆኖ እንዲሰራ የተመደበ። 3. በአንድ የውድድር ጨዋታ ወቅት የተመደበው ተጫዋች ቢጎዳ ወይም በሌላ ችግር መጫወት ባይችል በጎደለው እንዲተካ የሚመደብ ተጫዋች።

***ጠበቀ^1**

መጣብቅ ስ ማጣበቂያ።

ጣብቂያ ስ 1. ጠባብ የሆነ መተላለፊያ ቦታ። 2. ጭንና ጭን የሚነካካበት ቦታ። 3. (ዘይ.) አስቸጋሪ፥ አስጨናቂ ሁኔታ።

ተጣበቀ ግ 1. ተያያዘ፡ ተሳከከ፡ ተለጠፈ (በሙጫ፡ በሙቅ፡...)። 2. በሁለት ነገሮች መካከል ገብቶ ተጨቆነ፡ ታፈነ፡ ተጨነቀ።3. ልክክ፥ ልጥፍ አለ።

አጣበቀ ግ 1. ሳከከ፥ ለጠፈ፥ አያያዘ (በሙጫ፡ በሙቅ፡...)። 2.ያዘ (ሙጫው፡ ማጣበቂያው)። 3. በመካከል አስገብቶ አፈነ፥ አስጨነቀ። 4. ጠበበ፥ አልበቃ አለ (ልብስ፥ ጫማ)።

ማጣበቂያ ስ እንደሙጫ፡ ሙቅ ያለ የተለያዩ ነገሮችን ለማያያዝ ወይም ለመለጠፍ የሚያገለግል ነገር።

አጣብቂኝ ስ 1. ሰውነትን የሚያጣብቅ፥ ሰፊ ያልሆነ ልብስ። 2. በጣም አስጨናቂ፥ አስቸጋሪ ሁኔታ። 2. በሁለት ድንጋዮች መካከል የሚገኝ እጅግ በጣም ጠባብ የሆነ መተላለፊያ።

***ጠበቀ^2**

ጠበቃ ስ ባለጉዳይን ወክሎ በፍርድ ቤት የሚከራከር፥ የሚሟገት፥ ነገረ ፈጅ፥ አቡካቶ። የህግ ጠበቃም ይባላል።

ከጠበቃዬ ጠበቃዬ ይናገርልኝ፥ ይሟገትልኝ ለማለት የሚነገር አባባል።

ጠበቃ ወሰደ ለጉዳዩ የሚከራከርለትን ሰው አቆመ ወይም ወከለ።

ጠበቃ ገዛ ለጉዳዩ በፍርድ ቤት የሚከራከርለትን ጠበቃ አቆመ (ገንዘብ ከፍሎ)።

ጥብቅና ስ ሌላን ሰው ወክሎ የመሟገት፡ የመከራከር ተግባር።

ጥብቅና ቆመ ስ ሌላውን ሰው ወክሎ ተሟገተ፥ በፍርድ ቤት ተከራከረ።

ጠበበ ግ 1. አልበቃ አለ፥ አነሰ (ለምሳሌ ልብስ)። 2. ስፋት አጣ፥ አነሰ (ቦታ፥ መሬት፡..)። 3. ትንሽ ሆነ፥ አነሰ። *እድሉ እየጠበበ መጣ።*

ጠባብ ቅ1. ስፋት የሌለው። *ጠባብ ድልድይ/ጠባብ ክፍል።* 2. በልክ ያልተሰራ፡ በቂ ያልሆነ። *ጠባብ ልብስ።* 3. ውሱን የሆነ፡ አነስተኛ። *ሳዲስ ሰራተኛ ለመቅጠር ያለው እድል በጣም ጠባብ ነው።* 4.የተጠጋጋ፥ የተቀራረበ። *ውድድሩን ያሸነፉት በጠባብ የነጥብ ልዩነት ነው።*

ጠባብ ብሄረተኛ ቅ ለጎሳው ብቻ የሚያስብና የሚያደላ፥ በሌላው ላይ ጥላቻ የሚያሳይ።

ጠባብ ብሄረተኝነት ስ የጠባብ ብሄረተኛ አቋምን የያዘ አመለካከት።

ጠባብ አስተሳሰብ (አመለካከት) ጥልቀት የሌለው፥ በስፋት የማይገነዘብ እርቆ ማየት የጎደለው።

ጥበት ስ ሰፊ ያለመሆን፥ መጥበብ፥ የስፍራ ወይም የቦታ ማነስ።

ተጣበበ ግ ተጨናነቀ፥ ተፋፈገ።

አጠበበ ግ 1. ስፋቱን ቀነሰ፥ አሳነሰ፥ ጠባብ አደረገ። 2. ያለመጠኑ አሳንሶ ሰራ ወይም ሰፋ (ሊብስን፡ ጫማን)።

አጣበበ ግ 1.አጨናነቀ፥ መፈናፈኛ ቦታ አሳጣ። 2.ስፍራን ወይም ቦታን ሞላ፥ ያዘ። *ዝሆውን ያጣበበው የኮንትሮባንድ ዕቃ ነው።*

***ጠበበ**

ጠቢብ ቅ ብልህ፡ አዋቂ።

ጥበብ ስ 1. ብልሃት፥ እውቀት፥ ዘዴ። 2. በተለያየ ዲዛይንና ቀለም የሚሰራ የሃበሻ ልብስ ጥለት።

በጥበብ ተው.ግ. በዘዴ፥ በብልሃት።

ጥበበኛ ቅ አዋቂ፥ ብልሃተኛ፥ ዘዴ የሚያውቅ።

ተጠበበ ግ (በፍልስፍና፥ በእውቀት፥..) ተራቀቀ፥ ተፈላሰፈ።

ጠበንጃ "ጠመንጃ" ን ተመ.

ጠበኛ "ጠብ" ስር ተመ.

ጠበደለ ግ ወፈረ፥ወደለ።

ጠብደል ቅ ወፍራም፥ ወደል።

አጠበደለ ግ በጣም አወፈረ፥ አወደለ።

ጠበጠበ ግ 1. ገረፈ፥ ሸነቆጠ። 2. በቀስታ መታ መታ አደረገ።

ጥብጠባ ስ (ክር.) በክርስቶስ ላይ የተፈፀመውን ግርፋት ለማሰብና የስቃዩ ተካፋይ የመሆንን እምነት በምሳሌ ለማመልከት፥ የስቅለት በአል በሚከበርበት እለት ቀሳውስት የምእመናኑን ጀርባ በወይራ ዝንጣፊ በቀስታ መታ መታ በማድረግ እያንዳንዱ ምእመን ምን ያህል መስገድ እንዳለበት ትእዛዝ የሚሰጡበት ስርአት።

ጥብጥባት ስ የግርፋት ምልክት፥ ሰንበር።

ጠቢብ "*ጠበበ" ስር ተመ.

ጠባ^1 ግ መገመገ፥ መጠመጠ(ጡትን)።

አጠባ ግ ጡጦ በመስጠት መገበ።

አጠባች ጡት በመስጠት መገበች።

አጥቢ እንስሳት ስ ልጆቻቸውን ጡት በማጥባት የሚያሳድጉ እንስሳት።

ጠባ^2 ግ 1. ነጋ፥ ብርሃን ሆነ፥ ወገግ አለ

(ሌሊቱ፥ ጨለማው)። 2. ገዛ፥ ባተ። *መስከረም ጠባ።*

ጥቢ ስ ክረምት አልፎ መስከረም እንደገባ ያለው ጊዜ።

ጥባት ስ ንጋት።

አጥቢያ ስ ንጋት።

አጥቢያ ኮከብ ስ ንጋት ላይ ጎላ ብሎ የሚታይ ኮከብ።

ጠባ^3 ግ አረደ፥ ብልት አወጣ (ለምሳሌ ፍየልን)።

ጠባሳ "ጠበሰ" ስር ተመ.

ጠባቂ "ጠበቀ^1" ስር ተመ.

ጠባቃ "ጠበቀ^2" ስር ተመ.

ጠባብ "ጠበበ" ስር ተመ.

ጠባይ ስ 1. አመል፥ ባህርይ። 2. አንድ እቃ፥ መሳሪያ ወይም መኪና በትክክል የሚሰራበት ሁኔታ፥ ዘዴ። *የመኪናዋን ጠባይ ያውቀዋል።* 3. ሁናቴ። *የአየር ጠባይ።*

ጠባዩ ተለወጠ 1. ጠባዩ ተበላሸ። 2. በፊት የነበረውን ጠባይ ቀየረ።

የጠባይ ጉድለት የጠባይ ብልሹነት።

ጠብ ስ ጥል፥ አምባጓሮ።

ጠብ አበቀለ /አነሳ ተጣላ፥ ጥል ጀመረ።

ጠብ ጫረ ነገር ቆሰቆሰ ፥ ተነኮሰ።

ጠበኛ ቅ 1. ጥለኛ፥ ባላጋራ፥ ባላንጣ። *ከሰውየው ጋር ጠበኛ ነኝ።* 2.ጠብ ወይም አምባጓሮ የሚወድ፥ ነገረኛ።

ጠብ̈

ጠብ̈ታ ስ በአንድ ጊዜ ጠብ የሚል የተወሰነ መጠን ያለው ፈሳሽ (የመድሃኒት ወይም የሌላ ነገር)።

ጠብ̈ አለ ግ መሬት፥ እቃ፥... ላይ ወደቀ፥ አረፈ (የፈሳሽ ነጠብጣብ ወይም ሌላ ነገር)።

ጠብ̈ አይለውም ስስታም፥ ጩቅ ነው።

ጠብ̈ አይልም አይጠራቀምም። *የዛሬው ስራ ጠብ አይልም።*

ጠብ̈ አደረገ ግ በትንሹ ጣለ፥ አፈሰሰ፥ አወረደ። 2. ገደለ። *ወጋ ጠብ አደረገው።*

ጠብ̈ እርግፍ አለ በደስታ ተቀበለ፥ አስተናገደ፥ ተሽቆጠቆጠ።

ጠብ̈ እርግፍ አድርጎ ተወ ፈፅሞ፥ ጨርሶ ተወ።

ጠብ̈ ጠብ̈ አለ ግ ተንጠባጠበ።

ጠብ̈ ጠብ̈ አደረገ ግ አንጠባጠበ።

ተንጠባጠበ ግ ቀስ እያለ በትንሽ በትንሹ ወረደ፥ ፈሰሰ። 2.ቀስ እያለ መጣ፥ ተገኘ። *ሰው እየተንጠባጠበ መጣ።*

አንጠባጠበ ግ 1. በትንሽ በትንሹ አፈሰሰ፥ አወረደ፥ ጣለ። 2. አልፎ አልፎ አወረደ፥ ወረወረ፥ ጣለ። 3. በየቦታው አዝረከረከ፥ በተነ።

ጠብራራ "*ጠበረረ" ስር ተመ.

ጠብታ "ጠብ̈" ስር ተመ.

ጠብደል "ጠበደለ" ስር ተመ.

ጠቦት ስ ጡት መጥባት ያቋረጠና ከመጠኑ አነስ ያለ የበግ ወይም የፍየል ግልገል።

ጠነሰሰ ግ 1. ጠላ ለመጥመቅ፥ አረቄ ለማውጣት፥... ብቅልና ጌሾን በጠበጠ፥ አዋሃደ። 2. ወጠነ፥ አዘጋጀ (ደባን፥ ተንኮልን፥...)።

ጠንሳሽ ቅ አቀናባሪ፥ ጀማሪ፥ ወጣኝ (ሴራን፥ አድማን...)።

ጥንስስ ስ 1. የጠላ ጠመቃ ጅምር (የጌሾና የብቅል ብጥብጥ)። 2. የአንድ ነገር ወይም ተንኮል ውጥን፥ እቅድ።

ጥንስስ መሰለ ዳመና መሰለ፥ ጠቆረ።

ተጠነሰሰ ግ ታቀደ፥ ተወጠነ፥ ተቀነባበረ (ሴራ፥ ተንኮል፥...)።

ጠነቀለ ግ በጥቂቱ ወይም በትንሹ ቆነጠረ (ቅቤን፥ ማርን፥...)።

***ጠነቀረ**

ጥንቅር ስ ጥርቅም፥ ስብስብ።

ተጠናቀረ ግ ተጠራቀመ፥ ተሰበሰበ።

አጠናቀረ ግ አጠራቀመ፥ ሰበሰበ።

ጠነቀቀ ግ እንዳይበላሽ፥ ውጤቱ መጥፎ እንዳይሆን፥... ጥንቃቄ አደረገ። *ስራህን ጠንቅቀህ ስራ።*

ጠንቅቆ ያውቃል ሙሉ በሙሉ ወይም በደንብ አድርጎ ያውቃል።

ጠንቃቃ (ጥንቁቅ) ቅ ዝርክርክ ያልሆነ፥ ብልህ፥ አስተዋይ፥ ልባም።

ጥንቃቄ ስ አንድ መጥፎ ነገር ከመፈፀሙ ወይም ከመድረሱ በፊት ወይም ብልሽት፥ ስህተት፥ ችግር፥... እንዳይፈጠር ለመከላከል የሚደረግ ትኩረት፥ ዝግጅት፥ እንክብካቤ።

ጠንቀቅ አለ ግ ተጠነቀቀ።

ተጠነቀቀ ግ 1. ተዘጋጀ (መጥፎ ሁኔታን ለመከላከል)። 2. አደጋ፥ ክፉ ነገር፥ ብልሽት፥... እንዳይደርስ ጥንቃቄ አደረገ።

ተጠናቀቀ ግ ተፈፀመ፥ ተከናወነ፥ ተሰርቶ አለቀ። *ሴሚናሩ ትናንት ተጠናቀቀ።*

አጠናቀቀ ግ አከናወነ፥ ፈፀመ፥ ጨረሰ።

አስጠነቀቀ ግ 1. አስገነዘበ፥ ማሳሰቢያ ሰጠ። 2. ጥንቃቄ እንዲደረግ አዘዘ።

ማስጠንቀቂያ ስ 1. አንድ ነገር መደረግ

እንዳለበት ወይም እንደሌለበት ለማሳወቅ በፅሁፍ ወይም በቃል የሚሰጥ ማስገንዘቢያ፣ ትእዛዝ። 2. ጥንቃቄ እንዲደረግ የሚሰጥ ምልክት።

በማስጠንቀቂያ ታለፈ ጥፋቱን ሌላ ጊዜ ቢደግም መጥፎ ሁኔታ ወይም ቅጣት ሊከተል እንደሚችል ተገልፆለት ለጊዜው ይቅርታ ተደረገለት።

ጠነቆለ^1 ግ በአስማት፣ በጥንቆላ ይህ ይሆናል ብሎ ተነበየ፤ ተናገረ።

ጠንቋይ ስ በአስማት ወይም ዛጎል፣ ጠጠር በመጣል ይህ ይሆናል ብሎ የሚናገር፣ የሚተነብይ፤ እንዲሁም በአስማት፣ በመተት አማካይነት የተለያዩ አስገራሚ ድርጊቶችን የሚፈፅም ነው ተብሎ የሚነገርለት ሰው።

ጥንቆላ ስ ወደፊት እንዲህ ይሆናል ወይም ይደረጋል ብሎ የመናገርና እንዲሁም በአስማት ወይም በድግምት፣... አማካይነት የተለያዩ አስገራሚ ድርጊቶችን የመፈፀም ተግባር።

አስጠነቆለ ግ ኮከብ አስቆጠረ፤ ስለ እድሉ ወይም ስለሚያጋጥመው ሁኔታ ለማወቅ ወይም መልካም ነገር እንዲያጋጥመው ጠንቋይ ዘንድ ሄዶ ጠየቀ፣ አስጠየቀ።

ጠነቆለ^2 ግ ወጋ፣ ደነቆለ። *እንጨት አይኗን ጠነቆላት።*

*ጠነበረ

ጠንባራ ቅ (ስድብ) እውር፣ ደንባራ።

ጠንባራ ሽሮ (የን. አነ.) ቅባት የሌለውና በጥሩ ሁኔታ ያልተሰራ የሽሮ ወጥ።

ተጠናበረ ግ ተደናበረ።

አጠናበረ ግ 1.አደናበረ። 2. በጥፊ መታ፣ አሎሰ፤ አጠናገረ።

ጠነበሰ ግ በጥፊ መታ፣ አሎሰ።

ጠንባሳ ቅ (ስድብ) ጨንባሳ፣ ደንባራ።

አጠናበሰ ግ 1. አጨናበሰ፣ አደናበረ። 2. በጥፊ መታ፣ አሎሰ።

ጠነበዘ ግ 1. በጣም ሰከረ። 2. ታወረ፣ ደንባዛ ሆነ።

ጠንባዛ ቅ (ስድብ) 1. ደንባዛ፣ ሰክሮ የሚደናበር። 2. አይኑ የማያይ ።

ጥንብዝ አለ ግ በጣም ሰከረ።

ጠነባ ግ ገማ፣ ሸተተ።

ጥንብ (ጥምብ) ቅ 1. የበሰበሰ፣ የገማ። 2. (ስድብ) ቆሻሻ፣ ግማታም።

ጥንቡን ጣለ ረከሰ፤ የሚፈልገው ወይም የሚገዛው አጣ።

ጥንብ አንሳ ስ የሞተ እንስሳን ስጋ የሚበላ አሞራ፤ጆሬ አሞራ።

ጥንባት ስ መጥፎ ሽታ፣ ግማት።

አጠነባ ስ አገማ፣ መጥፎ መጥፎ እንዲሸት አደረገ።

ጠነነ ግ 1. ዘንበል አለ፣ አገደደ። 2. ጠመመ፣ ከፋ። 3. ከበደ፣ አዋኪ ሆነ፣ አቃተ። *ትምህርቱ ጠነነኝ።*

ጠናና ቅ 1. ዘንበል ያለ፣ገዳዳ። 2. ጠማማ፣ ከፉ።

አጠነነ ግ 1. አዘነበለ፣ አገደደ። 2. ከፋ፣ ጠመመ፣ ለገመ። 3. አከበደ፤ አዋኪ ወይም አስቸጋሪ አደረገ።

ጠነከረ ግ 1. በረታ፣ ጎበዘ። *ትምህርትህን ጠንክረህ ተማር።* 2. ጠና። *ለቅሶው ጠንክሯል።* 3. አየለ። *ጠላት እየጠነከረ መጣ ።* 4. ጠጠረ፣ ከረረ። 5. ከበደ፣ አስቸጋሪ ሆነ።

ጠንካራ ቅ 1. ብርቱ፣ ጎበዝ። *በችግር የማይረታ ጠንካራ ሰው።* 2. ጠጣር፣ ከራራ፣ ጠባቃ።3.በቀላሉ የማይበሳሽ፣ የማይሰበር፣... ጥሩ (እቃ፣ ...)።

ጥንካሬ ስ ብርታት። 2. ጉልበት፤ አቅም።

ተጠናከረ ግ 1. ተበረታታ፣ ጎበዘ። 2. ሃይሉ ጨመረ ወይም ከበፊቱ የተሻለ ወይም የበለጠ እንዲሆን ተደረገ።

አጠነከረ ግ 1. አበረታ፣ ሃይል ሰጠ። 2. አስቸጋሪ አደረገ።

አጠናከረ ግ ሃይል ጨመረ ወይም ከበፊቱ የበለጠ እንዲሆን አደረገ።

ማጠናከሪያ ቅ ቀደም ሲል በነበረው ላይ እየተጨመረ የነበረውን የበለጠ የሚያሻሽል፣ የሚያፀና። *የማጠናከሪያ ትምህርት/ የማጠናከሪያ ላምጅ።*

ጠነዛ ግ 1.እሳት ስለአነሰው በደንብ ሳይበስል ቀረ። 2.አረጀ፣ ገረጀፈ። 3. (ዘይ.) ተሰላቸ፣ እጅ እጅ አለ።

ጠናዛ ቅ (ስድብ) ያረጀ፣ የሸመገለ፣ የገረጀፈ።

አጠነዛ ግ በደንብ ሳያበስል ቀረ።

*ጠነገ

ጥንግ ስ ከጠፍር ተጠርዞ የተሰራ ፍር።

አጠነጋ ግ 1. በጥፊ፣ በዱላ፣... መታ። 2. ቀላ፣ ለጋ (ጥንግን)።

*ጠነገረ

ጠንጋራ ቅ 1. ሸውራራ፣ አይኖቹ በየፊናቸው ወደ ተለያየ አቅጣጫ የሚመለከቱ የሚመስል። 2. እውር።

ተጠናገረ ግ 1. ተንሸዋረረ። 2. ታወረ።

አጠናገረ ግ 1. አንሸዋረረ። 2. እውር አደረገ። 3. በጥፊ መታ፣ አጠናፈረ።

ጠነጠነ^{1} ግ አረጀ፥ ሸመገለ።

ጥንጣን ስ 1. እንጨት የሚበላ የትል አይነት፡ ቁንቁን፡ ነቀዝ።2. ነቀዝ ወይም ቁንቁን ከበላው እንጨት የሚወጣ ዱቄት መሰል ነገር።

ጥንጣን ሆነ በጣም ደቀቀ፡ ዱቄት ሆነ።

ጠነጠነ^{2} ግ 1. መታ፡ ደበደበ። 2. ወረወረ፡ በተነ። *ሃብቱን ጠነጠነው።*

*ጠነጠነ

ጥንጥን ስ ልቃቂት፡ ድውር።

አጠነጠነ ግ 1. አጸወረ። 2.ጠመጠመ፡ ጠቀለለ (ለምሳሌ ፈትልን)። 3.(ዘይ.) ተበተበ፡ ሸረበ (ነገርን)። *ነገር ማጠንጠን ይወዳል።*

ጠነፈፈ ግ ጠፈፍ ወይም መጠጥ አለ።

ጥንፈት ቅ 1. ከንፍሮ፥ ከአሹቅ፥... ላይ የሚወገደውና ሲጠነፈፍ የሚወጣው ፈሳሽ ።2. እላቂ፡ ሙጣጭ፡ ጭላጭ (የፈሳሽ)።

አጠነፈፈ ግ 1. አንጠፈጠፈ፥ አፈሰሰ፡ አስወገደ (ለምሳሌ ውሃን ከንፍሮ ውስጥ)። 2. ጨረሰ፡ አሟጠጠ።

ማጠንፈፊያ ስ ፈሳሽን ለብቻው (ከንፍሮ፥ ከሥስታ፥...) ለይቶ ለማፍሰስ ወይም ለማጥለል የሚያስችል እቃ፡ ወንጠፍት።

ጠና ግ ጠነከረ፡ በረታ።

መጥኔ ይስጥህ ብርታቱን፡ ጥናቱን ይስጥህ ለማለት የሚነገር አባባል።

በጠና በሃይል፡ በብርቱ። *በጠና ታሟል።*

ፅኑ (ጥኑ) ቅ 1. ብርቱ፡ ጠንካራ። 2. ከባድ፡ ከፍተኛ። *ፅኑ ረሃብ።*

ፅኑ እስራት ስ ከሌሎች እስረኞች ይበልጥ እስራቱ የሚከብድበት የእስራት አይነት።

ፅናት(ጥናት) ስ ጥንካሬ፥ ብርታት፥ ችግርን መከራን የመቋቋም ችሎታ።

ጠና አለ ግ ጠነከረ፥ በረታ።

ጠና ያለ ቅ በሰል ያለ፥ በጣም ያላረጀ (ለሰው)።

ተፅናና ግ ተበረታታ፡ ተረጋጋ (ከሃዘን)።

አፅናና (አጥናና) ግ አረጋጋ፥ አበረታታ።

ማፅናኛ (ማጥናኛ) ስ የሃዘን ማስረሻ።

አፅናኝ (አጥናኝ) ቅ አበረታች፡ የሚያበረታታ፡ የሚያረጋጋ።

*ጠና

ጥናት ስ 1. የተማሩትን በመከለስ፡ በማንበብ፡ በመወያየት ጉዳዩን ይበልጥ የመረዳት ሂደት፡ ቅፀላ። 2. ስለአንድ ነገር በይበልጥ ለማወቅ ወይም ለመረዳት የሚደረግ የንባብ ወይም የክለሳ ተግባር። 3. በአንድ ጉዳይ ላይ በማተኮር ስለ ሁኔታው፡ ስለ ችግሩ፡ ስለ መፍትሄው ትንተናና ማጠቃለያ የሚሰጥ የምርምር ተግባር ወይም ውጤት።

ተጠና ግ 1. ታወቀ፥ ግልፅ ሆነ፡ ስለምንነቱ ይበልጥ ታወቀ። 2. በምርምር፥ በጥናት ግልፅ ሆነ ወይም ተገመገመ።

ተጠናና ግ ጠባይ ለጠባይ ወይም ባህሪ ለባህሪ ተዋወቀ።

አጠና ግ 1. የተማረውን በመከለስ ወይም እንደገና በማንበብ ይበልጥ አወቀ፥ ተረዳ፥ ተገነዘበ። 2. ጥናት፥ ምርምር አደረገ።

አጥኚ ስ ስለአንድ ነገር ሁኔታና ምንነት መርምሮና አጥንቶ የሚያቀርብ ተመራማሪ።

አስጠና ግ ስለአንድ ነገር ጥናት እንዲካሄድ አደረገ።

ጠናና "ጠነነ" ስር ተመ.

ጠናዛ "ጠነዘ" ስር ተመ.

ጤ ስ ፅኑ ረሃብ (አቅም የሚያሳጣ፥ የሚጥል)።

ጤያም ቅ (ስድብ) ረሃብ ያጠቃው፥ ችጋራም።

ጠንሳሽ "ጠነሰሰ^{1}" ስር ተመ.

ጠንቀኛ "ጠንቅ" ስር ተመ.

ጠንቃቃ " ጠነቀቀ" ስር ተመ.

ጠንቅ ስ 1. የበሽታ ወይም የሌላ መጥፎ ነገር ውጤት። 2. ሰበብ፡ መዘዝ (የበሽታ፡ የመጥፎ ነገር፥...)።

ጠንቀኛ ቅ መዘዘኛ፡ መጥፎ ውጤት የሚያስከትል።

ጠንቋይ "ጠነቆለ" ስር ተመ.

ጠንበለል(ጠምበለል) ስ 1.እንደሃረግ ራሱን ችሎ የማይቆምና ጥሩ መአዛ ያለው የእፅዋት አይነት። 2. (ዘይ.) ለግላጋ (ወጣት)።

ጠንባራ "*ጠነበረ" ስር ተመ.

ጠንባሳ "ጠነበሰ" ስር ተመ.

ጠንባዛ "ጠነበዘ" ስር ተመ.

ጠንካራ "ጠነከረ" ስር ተመ.

ጠንገሎ "ጠረንገሎ" ን ተመ.

ጠንፍ ስ ዳርቻ፡ ጠርዝ።

ጥንፍ (ፅንፍ) ዝ.ከ.

አጥናፍ (አፅናፍ) ስ ዳርቻ፡ ጠንፍ።

ከአጥናፍ እስከ አጥናፍ ከዳር እስከ ዳር፡ ከጠረፍ እስከ ጠረፍ፥ በመላው ሃገር።

*ጠወለወለ

ጥውልውል አደረገ ግ አጥወለወለ።

አጥወለወለ ግ አቅለሸለሸ፡ አዞረ።

ጠወለገ ግ 1. ልምላሜ አጣ፥ እንደመድረቅ አለ። 2. ተጎሳቆለ።

ጠውላጋ ቅ 1. የጠወለገ፡ እንደ መድረቅ ያለ (ተክል)። 2. (ዘይ.) የተጎሳቆለ፥ ሃይል ያነሰው፥ ደካማ።

ጠወረ "ጦረ" ን ተመ.

ጠዋት "ጧት" ን ተመ.

ጠውላጋ "ጠወለገ" ስር ተመ.

ጠዘጠዘ ግ 1. ጠቅ ጠቅ እያደረገ አመመ፡ ነዘረ (ቁስል)። 2. ነደፈ፡ ወጋ፥ ጠቅ አደረገ (ለምሳሌ ንብ፥ ተርብ)። 3. (ዘይ.) ጨቀጨቀ፡ ነተረከ (በነገር፡...)።

ጥዝጣዜ ስ እየቆየና ጠቅ ጠቅ እያደረገ የሚያም ወይም የሚነዝር ህመም።

ተጠዛጠዘ ግ 1.ተዋጋ፡ ተተጋተገ፡ ተቆናደደ (በጅራፍ፡ በቀስት፡ በጥይት፡...) ። 2. (ዘይ.) በነገር ተነታረከ፡ ተሰዳደበ።

ጠየመ ግ መልኩ በጥቁርና በቀይ መካከል ሆነ፥ ደበብ ያለ ቀለም ያዘ።

ጠይም (ብ.ቁ . **ጠያይም**) ቅ መልኩ ጥቁር ወይም ቀይ ሳይሆን መሃከለኛ ወይም ደበብ ያለ የሆነ(ሰው)።

አጠየመ ግ 1. በፊት ከነበረው ትንሽ ጠቆር አደረገ (መልክን)። 2. (ዘይ.) ፊትን አከፋ (ከጥላቻ የተነሳ)።

ጠየቀ ግ 1. የአንድን ሰው ወይም ነገር ምንነትና ማንነት፥ አድራሻ፥... ለመረዳት ወይም ለማወቅ ጥያቄ አቀረበ፥ መልስ ፈለገ። 2. አየ፥ ጎበኘ (በሽተኛን፥ እራስን፥...) ። 3. መረመረ፥ አውጣጣ። 4. አንድ ነገር እንዲደረግለት ወይም እንዲፈፀምለት ፍላጎቱን ነገረ። 5. ለጋብቻ ወይም ለወዳጅነት መፈለጉን ለተፈለገው ሰው ገለፀ። 6. አስፈለገ። *ስራ ለመቀጠር ዲግሪውን ጠየቀ/ህንፃውን ለመጨረስ ብዙ ገንዘብ ጠየቀ /ለድል ለመብቃት ብዙ መስዋእትነት ጠየቀ።*

መጠይቅ ስ ስለ አንድ ነገር መረጃ በሚሰበሰብበት ወቅት አስፈላጊውን መረጃ ሊያስገኙ የሚችሉ ጥያቄዎች ወይም ጥያቄዎቹን የያዘ ቅፅ።

ልጠየቅ በእሰጥ አገባ ሙግት ጊዜ ከሳሽ "ተጠየቅ" ሲል ተከሳሽ "ልጠየቅ" በማለት የክሱን ቃል ለመስማት ዝግጁ መሆኑን ይገልፅበት የነበረ አባባል።

ጠያቂ ቅ 1. ዘመድን፥ ወዳጅን፥ ህመምተኛን፥... የሚጎበኝ። 2. ጥያቄ አቅራቢ።

ጠያቂዬ ነው በየጊዜው የሚጎበኘኝ፥ ችግሬን የማዋየውና የሚረዳኝ ነው።

ጥያቄ ስ ስለ አንድ ነገር ለማወቅ፥ ለመረዳት ወይም አንድ ነገር ለማግኘት በመፈለግ በቃል ወይም በፅሁፍ ለሚመለከተው የሚቀርብና መልስ የሚሻ ሃሳብ።

ጥያቄ አቀረበ ጠየቀ።

ተጠየቀ ግ 1. ጥያቄ ቀረበ ወይም ቀረበለት። 2. ሃላፊነት ውስጥ ገባ ። *በዚህ ውሳኔ እኔ እጠየቅበታለሁ።*

ተጠየቅ 1. በእሰጥ አገባ ሙግት ጊዜ ከሳሽ ተከሳሽን "ክሱን ስማና መልስ ስጥ" ለማለት ይናገረው የነበረ ቃል ወይም አባባል። 2. እርስ በርሳቸው የተያያዙና የማይፋለሱ ሃሳቦች ከአንድ መንደርደሪያ ሃሳብ በመመንጨትና ከርሱም ጋር በመያያዝ በተወሰኑ የአስተሳሰብ ህግጋት መሰረት ወደ ትክክለኛ መደምደሚያ የሚያመሩበት ሁኔታ።

ተጠያቂ ስ ሃላፊ፥ የጉዳዩ ባለቤት፥ ተጠሪ። 2.በሳል ምሁር፡ ሊቅ (ለሚቀርብለት ትምህርታዊ ጥያቄ አጥጋቢ መልስ ሊሰጥ የሚችል) ።

ተጠያየቀ ግ በተወሰነ ጊዜ እየተገናኙ ሃሳብ ተለዋወጡ፡ ተወያዩ፥ ተረዳዱ።

አጠየቀ ግ ማስረጃ ሆነ፥ አረጋገጠ። *ትናንት አለመምጣቱ ከሃሳባችን የተለየ መሆኑን ያጠይቃል* (የቆየ አባባል)።

አጠያየቀ ግ 1. አፈላለገ፥ እዲፈለግለት አደረገ (የሚሻውን ነገር ለማግኘት)። 2. አጠራጣሪ ሆኖ ተገኘ።

አጠያያቂ ቅ በግልፅ ያልታወቀ፡ አጠራጣሪ፡ አወዛጋቢ።

አስጠየቀ ግ በሃላፊነት አስከሰሰ፡ አስወነጀለ። *የህዝብን ገንዘብ ያለአግባብ ማባከን በህግ ያስጠይቃል።*

ጠያፍ ""*ፀየፈ" ስር "ፀያፍ"ን ተመ.

ጠይም "ጠየመ" ስር ተመ.

ጠይብ ስ 1.በድሮ ስርአት እንደ ሸማኔ፡ አንጥረኛ፥... ያሉትን ባለሙያዎች አንኳሰሰው የሚጠሩበት ቃል።2. ቡዳ።

*ጠደፈ

ጥድፊያ ስ ችኮላ፥ ፍጥነት (የስራ፡ የአካሄድ)።

ተጣደፈ ግ 1. ተቻኮለ (አንድን ነገር ቶሎ ወይም በፍጥነት ለማድረግ)። 2. በፍጥነት ወይም ቶሎ ቶሎ ተሰራ፥ ተካሄደ (አንድ ስራ)።

አጣደፈ ግ 1. አቻኮለ። 2. አዋከበ። 3.ቶሎ ቶሎ አፋጠነ (ስራን፥...)። 4. ፋታ ወይም ጊዜ የማይሰጥ ሆነ።

አጣዳፊ ቅ 1. አስቸኳይ፤ በቶሎ መካሄድ፡ መከናወን፥ መሰራት፥ መቅረብ፥... ያለበት። 2. ጊዜ የማይሰጥ (በአጭር ጊዜ ለሞት፥ ለጉዳት፥... የሚያደርስ)። *አጣዳፊ የተቅማጥ በሽታ።*

ጠዲቅ "ፀደቀ^{1}" ስር "ፀዲቅ"ን ተመ.

ጠጳ "ፀጳ"ን ተመ.

ጠጶ ስ እንጨትና ቅጠሉ ጌሾ የሚያህልና የሚመስል የእፅዋት አይነት።

ጠጀ(ጠጀተ) ግ ጠጅ ጣለ ወይም ጠመቀ።

ጠጅ ስ ማርና ጌሾን በማደባለቅ የሚዘጋጅ ቢጫ መልክና አልኮልነት ያለው መጠጥ።

ጠጅ ጣለ ጠጅ ጠመቀ ወይም አዘጋጀ።

ጠጅ ቀጂ ስ የጠጅ ቤት አሳላፊ፥ አስተናባሪ።

ጠጅ ቤት ስ ጠጅ የሚሸጥበትና የሚጠጣበት ቤት።

ጠጅ አሳላፊ ስ ጠጅን ለጠጪዎች የሚያድል ወይም የሚያቀርብ።

ጠጀ ሳር (ጠጅ ሳር) ስ ነጣ ያለ መልክ ይዞና እንደ እንግጫ ሆኖ የሚበቅል፥ ጥሩ ሽታ ያለው ሻካራ የሳር አይነት።

ጠገራ^{1} [ብር] ስ ብር ከሚባለው የማእድን አይነት የተሰራና በዱሮ ጊዜ ያገለግል የነበረ ገንዘብ።

ጠገራ^{2} ስ በአንድ በኩል ብቻ ስለት ያለው፥ ጫንቃው ወፍራም የሆነና ቀጥ ካለ እጀታ ላይ የሚሰካ መጥረቢያ።

ጠገራ^{3} ስ ለዶማ፥ ለመጥረቢያ፥ ለማረሻ፥... መስሪያ የሚያገለግል ድብልብል ብረት።

ጠገበ ግ 1. ሆዱ ሞላ፥ ረካ (በመብላ፥ በመጠጥ)። 2. (ዘይ.)ኩራ፥ ማንአለብኝ አለ፥ በትእቢት ተሞላ። 3. ፍቅሩን፥ ናፍቆቱን ተወጣ። 4. በብዛት አገኘ። *መሬቱ ዝናብ ጠገበ።*

—ጠገብ ቅ በበቂ ሁኔታ ያገኘ፥ የተጎናፀፈ፥... ለማለት የሚያገለግል ከፊል ቃል። *ውሃ ጠገብ / ጆሮ ጠገብ።*

ጥጉብ ቅ 1. ያረገዘች (ለአህያ፥ ለፈረስ)። 2. ወፍራም (ለመፅሃፍ)።

ጥጋብ ስ 1. የሆድ መሙላት፥ እርካታ (በምግብ፥ በመጠጥ)። 2. (ዘይ.) ኩራት፥ ትእቢት፥ ማን አለብኝነት፥ እብሪት። 3. የእህል ችግር የሌለበት ጊዜ። *ዘንድሮ ጥጋብ ነው።*

ጥጋበኛ ቅ ትእቢተኛ፥ እብሪተኛ።

ተጣገበ ግ ፍቅሩን፥ ናፍቆቱን ተወጣ፥ ጨረሰ (እርስ በርስ)።

አጠገበ ግ 1. ሆዱ እስኪሞላ አበላ፥ አጠጣ። 2. አረካ (የተበላው ምግብ፥ መጠጥ)። 3. ትእቢተኛ፥ እብሪተኛ፥ ኩራተኛ እንዲሆን አደረገ። 4. በብዛት በመስጠት፥ በማስገኘት፥ በማቅረብ፥... አረካ። *ዝናቡ አጠገበ።*

አጥጋቢ ቅ የሚያረካ፥ ደስ የሚያሰኝ፥ ብቃት ያለው፥ ...።

ጠገነ ግ 1. የተሰበረን አጥንት አስሮ እንዲድን አደረገ። ቅ 2. የተጎዳ፥ የተበላሸን ነገር አስተካከለ፥ አበጀ፥ አደሰ፥ ደህና አደረገ። 3. (ዘይ.) ጠቀመ፥ ደገፈ፥ ረዳ።

ጠጋኝ ስ 1. የእድሳት ስራ የሚሰራ የእጅ ባለሙያ። ቅ 2. መሰረታዊ ለውጥ ሳይሆን የነበረውን ሁኔታ በመጠኑ በማሻሻል ብቻ ለውጥ ለማድረግ የሚሞክር የፖለቲካ አዝማሚያ ያለው።

ጥገና ስ የተሰበረ፥ የተጎዳ፥ የተበላሸ እቃን ማስተካከል፥ ማደስ፥ ማበጀት።

ጥገናዊ ለውጥ ስ መሰረታዊ ያልሆነና በነበረው ላይ ብቻ መጠነኛ የሆነ መሻሻልን የሚያስከትል ለውጥ።

ጥግን ቅ ተሰብሮ፥ ተበላሽቶ የነበረና የተሰራ ወይም የታደሰ (እቃ)።

አስጠገነ ግ አሰራ፥ አስበጀ(የተበላሸን፥ የተሰበረን እቃ)።

ጠገነነ ግ ዘገነነ፥ ሰቀጠጠ፥ አስቆጣ።

ጠገገ ግ መበጥ አለ፥ ደረቀ (ቁስል፥ ጭቃ)።

ጠገግ^{1} ስ ፍራሽ ወይም ጉዝጓዝ የሌለው የእንጨት አልጋ፥ ቆጥ።

ጠገግ^{2} ስ የሰንሰለት አንዷ ሞላላ ቀለበት።

ጠጉር "ፀጉር"ን ተመ.

***ጠጋ**

ጥግ (ጥጋት) ስ ተገን ያለው ወይም በኮረብታ፥ በግድግዳ፥... አጠገብ ወይም ስር የሚገኝ ቦታ።

ባለጥግ ባለወገን። *ጠላቴ ባለጥግ ስለሆነ ልረታው አልቻልኩም።*

ጥግ ያዘ 1. ተጠጋ፥ ጥግ ላይ ሆነ። 2.ደህና ቦታ ወይም ስፍራ፥... ያዘ።

ጥጋጥግ ስ የተራራ፥ የኮረብታ፥ የገደል ስር።

ጥገኛ ቅ 1. ራሱን ያልቻለ፥ በሌላ እርዳታ የሚኖር። 2. በሌላው አካል ወይም ድርጅት ጥላ ስር የሚንቀሳቀስ (ንኡስ ክፍል)። 3. ኑሮው፥ ህልውናው፥ ህይወቱ በሌላው ላይ የቆየ (የነፍሳት ወይም የእፅዋት አይነት)።

ጥገኛ ሃረግ ስ የማያስር አንቀፅ ያለበት የአረፍተ ነገር ንኡስ ክፍል።(ለምሳሌ "ከሄድኩ አልመጣም"። በሚለው አ.ነገር ውስጥ "ከሄድኩ" የሚለው ጥገኛ ሃረግ ነው)።

ጠጋ አለ ግ ቀረብ አለ (በአካል፥በስሜት፥ በአስተያየት፥ በመጠን፥...)።

ጠጋ አደረገ ግ አቀረበ፥ አስጠጋ።

ተጠጋ ግ 1. ቀረበ፥ ጠጋ አለ። 2. ጥገኛ ሆነ፥ በሌላ ሰው እርዳታ ኖረ። *ከሃብታም ተጠግቶ ይኖራል።* 3.አከለ፥ ደረሰ።*የተሸለሙት ሰዎች ወደ ሺህ ተጠግተዋል።* 4. ተከለለ፥ ተገን አደረገ።*ጅብን ሲወጉ በአህያ ይጠጉ።*

አይጠጋውም ምንም ያህል ቢበላ ለውነት አይሆነውም፤ አይጠረቃም።

መጠጊያ ስ 1. ከአደጋ መሸሸያ፥ ከፉ ጊዜን ማሳለፊያ (ሰው፥ ቦታ፥…)። 2. መጠለያ።

ተጠጋጋ ግ 1. ተቀራረበ። 2. ከአንድ በታች የሆነ ክፍልፋይ ቁጥር ከግማሽ በላይ በመሆኑ ወደሙሉ ቁጥርነት ተለወጠ (ለምሳሌ፥ 5.6 ሲጠጋጋ 6.00 ይሆናል)።

ተጣጋ ግ ከሳ፥ ጭገገ።

አጠጋጋ ግ 1. አቀራረበ። 2. ከግማሽ በላይ የሆነ ክፍልፋይ ቁጥርን ወደ ሙሉ ቁጥር ለወጠ።

አጣጋ ግ 1. አጋጨ፥ አላተመ፥ መታ። 2. ክፍልፋይ ቁጥርን ወደ ሚቀርበው መጠን አሸጋሸገ፤ ለወጠ። (ለምሳሌ፥ 2.7 ሲጣጋ 3. ይሆናል)።

አስጠጋ ግ 1. አቀረበ፤ አንዱን ነገር ከሌላ ጎን ወይም አጠገብ አስቀመጠ። 2. መጠጊያ ሆነ፤ ረዳ።

ጠጋኝ "ጠገነ" ስር ተመ.

ጠጠረ ግ 1. ጠነከረ፥ በረታ፥ ጠና። 2. ደደረ፥ እንደ ጠጠር ሆነ።3. (ዘይ.) ከበደ፤ ቀላል አልሆን አለ።

ጠጠር ስ 1. ትናንሽ ወይም ጥቃቅን ድንጋይ። 2.እንደ ልቅምሽ፥ ገበጣ፥ ዳማ፥… ያሉ ጨዋታዎችን ለመጫወት የሚያገለግሉ መጫዎቻዎች።

ጠጠር ጣይ ስ ጠጠር እየበተነ ወይም እየጣለ ይህ ይሆናል ወይም ይህ ይደረጋል የሚል ጠንቋይ ።

ጠጣር ቅ 1. ጠንካራ። 2. ፈሳሽ ያልሆነ 3.(ዘይ.) ከባድ፥ አስቸጋሪ።

ጥጥር ዝ.ከ.

ጠጣ ግ 1. ወደ ሆዱ አስገባ፤ ዋጠ፥ ፉት አለ፥ ጨለጠ (ፈሳሽን)። 2. ወሰደ፤ ተጎነጨ (አልኮል መጠጥን)። 3. አጨሰ፤ ሣበ፤ መጠጠ። (ሲጋራን፤ ትንባሆን)። 4.መጠጠ። *ወረቀቱ ቀለሙን ጠጣው።* 5. ውሃ ተጨመረበት፥ ፈሰሰበት (አትክልት፤ ግንብ፤…)።

መጠጥ ስ 1. በፈሳሽ መልክ ተዘጋጅቶ የሚጠጣ ነገር። 2.አልኮልነት ያለውና የሚጠጣ ፈሳሽ። *መጠጥ ሲበዛ ለጤና ጠንቅ ነው።*

መጠጥ አወረደ መጠጥ በሳጥን ወይም በጅምላ ገዛ (ለመጠጥ ንግድ ቤት)።

መጠጫ ስ 1. እንደ ኩባያ፤ ዋንጫ ያለና ለመጠጫነት የሚያገለግል እቃ። 2. እንደ ሸንበቆ ያለ የጋያ መሳቢያ (የትንባሆ ጭስ መማጊያ)።3. ለመጠጥ የሚሆን ገንዘብ። *መጠጫ ሲያጣ በጊዜ ይገባል።*

የመጠጥ ውሃ ስ ለመጠጥ የሚሆን ውሃ።

ጠጪ ቅ 1. ሰካራም፤ መጠጥ የሚያበዛ። ስ 2. ወደ መሸታ ቤት በመሄድ መጠጥ እየገዛ እዚያው ቁጭ ብሎ የሚጠጣ ደንበኛ።

ተጣጣ ግ 1. ተቻቻለ፥ እዚያው (በዚያው ሂሳብ) ተወራረደ፥ ተከፈለ። 2. እየተጠራራ፥ እየተገባበዘ ጠጣ (ቡናን፥ ጠበል ጠዲቅን)።

አጠጣ ግ 1. ውሃን ወይም ሌላ ፈሳሽ ነገርን እንዲጎነጭ ሰጠ። 2. ውሃ ጨመረ፥ አፈሰሰ (አትክልት፥ ግንብ፥… ላይ)። 3. መጠጥ ጋበዘ። 4. በገበጣ ጨዋታ ጊዜ በውጉ ላይ ጠጠር ጨመረ፤ ወይም በካርታ ጫወታ ጊዜ በበላው ካርታ በተጨማሪ ተመሳሳይ ቁጥር ያለውን ካርታ ጨመረ።

አስጠጣ ግ (ያራዳ አነ.) እንዲታወቅ አደረገ፥ አጋለጠ።

ጠፈረ^{1} ግ 1. አጥብቆ አሰረ፤ ቀፈደደ። 2. ማገረ፥ አዋቀረ፥ ታታ (የቤትን ጣራ፥ ግድግዳ)።

ጠፍር ስ ከከብት ቆዳ ተተልትሎ የተዘጋጀ ማሰሪያ።

ጠፍር ነካሽ "ጫኝ" ስር "መጫኛ ነካሽ"ን ተመ.

ጠፈረ^{2} ግ በጥፊ መታ፥ አጮለ።

አጣፈረ (አጠናፈረ) ግ በጥፊ መታ፥ አጮለ።

ጠፈር ስ ከምድር ከባቢ አየር ውጪ ያለ ቦታ፤ ሰማይ።

ጠፈርተኛ ስ ለልዩልዩ ስራ ወይም ምርምር በመንኮራኩር ወደጠፈር የሚሄድ ወይም የሚላክ ሰው።

የጠፈር መንኮራኩር ስ በጠፈር ውስጥ መጓዝ የሚችል ሰው ሰራሽ በራሪ አካል።

ጠፈጠፈ ግ 1. ወፍራም ሊጥን በምጣድ ላይ ዘረጋጋ (ለመጋገር)። 2. የከብት እበት ኩበት እንዲሆን በመሬት ላይ በእጁ እየተመተመ ዘረጋጋ። 3. (ዘይ.) ደጋግሞ በጥፊ መታ።4. ጠፍጣፋ ወይም ዝርግ አደረገ (ደጋግሞ በመቀመጥ፥ በመምታት፥…)።

ጠፍጣፋ ቅ ድብልብል ወይም ሞላላ ያልሆነ፥ ዝርግ።

ጥፍጥፍ ስ 1. የተጠፈጠፈ የከብት እበት። ቅ 2. (ዘይ.) ድፍጥጥ፤ አፍንጫው ቀጥ ያላለ።

***ጠፈጠፈ**

ጠፈጠፍ ስ ዝናብ ከዘነበ በኋላ ከቤት ጣሪያ፥ ከዛፍ ቅርንጫፍ፤ ከቆንጥሳ ላይ የሚንጠባጠብ የዝናብ ውሃ፤ ፍሳሽ።

ተንጠፈጠፈ ግ እየተንጠባጠበ ፈሶ አለቀ፥ ደረቀ (ውሃ አዝሎ የነበረ ነገር)።

እንጠፈጠፈ ግ እያንጠባጠበ አፈሰሰ፣ አደረቀ (ፈሳሽን)።

እንጥፍጣፊ ቅ 1. እቃ ላይ የቀረ ትንሽ ፈሳሽ፣ ጭላጭ። 2. ሙጣጭ።

ጠፈፈ ግ መጠጠ፣ መድረቅ ጀመረ።

ጠፍታ ስ ዝርክርክነት የሌለበት ሁኔታ።

ጠፈፍ አለ ግ መጠጥ፣ ደረቅ አለ።

ጠፍ አለ ግ 1. መጠጠ፣ ደረቀ። 2. (ዘይ.) ንፁህ፣ ዝርክርክነት የሌለው ሆነ። *ጠፍ ያለች የቤት ወይዘሮ።*

ጠፋ[1] ግ 1. ታጣ፣ አልገኝ አለ፤ ወደ አለመኖር ተለወጠ። 2. ሳያሳውቅ ሄደ፣ ኮበለለ፣ አድራሻውን ሰወረ። 3. እልም አለ፣ ተደረገመ(አይን፣ እሳት፣...)። 4. ሞቶ ተወለደ ወይም እንደተወለደ ሞተ (ህፃን)። 5. ተበላሸ፣ መጥፎ ሆነ (ልብስ ወይም ሌላ እቃ)። 6. ተረሳ፣ ተዘነጋ።*ስሙ ጠፋብኝ።* 7. ምግባሩ፣ ጠባዩ ተበላሸ፣ ተለወጠ። 8. ወጪ ሆነ። *ለመስተንግዶ ብዙ ገንዘብ ጠፋ።* 9. ለቀቀ፣ ተወ። *ፍርሃቱ ጠፋለት።* 10. ሳይመጣ ወይም ሳይታይ ቀየ። *ሰሞኑን ጠፋህ፤ ላላገኘሁህም።* 11. ተሰረዘ፣ የማይታይ ወይም የማይነበብ ሆነ (ፅሁፍ፣...)።

የጠፋ የማይታወቅ። *ውሉ የጠፋ /መፍትሄው የጠፋ።*

መጥፎ ቅ 1. አስቀያሚ፣ የማያምር። 2. ክፉ፣ ተንኮለኛ፣ ጠባየ ብልሹ። 3. የማይስማማ፣ የማይመች፣ ጥሩ ያልሆነ(ጊዜ፣ ቦታ፣...)።

ጠፊ ቅ 1. ሟች። *ሁሉም ኣላፊ ጠፊ ነው።* 2. አላቂ። *ሃብት ጠፊ ነው።*

ጠፍ ቅ 1. ያልታረሰ፣ ያልለማ (መሬት)። 2. ለምነት የሌለው (መሬት)። 3. ባለቤት የሌለው (ብዙውን ጊዜ ለከብት)። *የጠፍ ከብት።*

ጠፍ ሆነ ባድማ ሆነ።

ጠፍ ከለም ቅ ከፊል ለም ከፊል ጠፍ የሆነ (መሬት)።

ጠፍ ጨረቃ ስ የጨረቃ ብርሃን የማይታይበት፣ ድፍን ጨለማ የሆነበት ሌሊት።

ጥፉ ቅ 1. ብልሹ፣ ጠባየ መጥፎ። 2. የማያምር፣ አስቀያሚ፣ ደስ የማይል (መልክ)።

ጥፋት ስ 1. ስህተት፣ ትክክል ያልሆነ ስራ። 2. ከህግ፣ ከደንብ ውጭ የተፈፀመ ድርጊት። *ተጫዋቹ ጥፋት ስለሰራ የቅጣት ምት ተሰጠ።* 3. ጉዳት፣ ብልሽት። *ጎርፉ በንብረት ላይ ጥፋት አደረሰ።*

ጥፋተኛ ቅ 1. ወንጀለኛ። 2. ስህተተኛ፣ በደል የፈፀመ።

ጥፌ ቅ ባለቤቱ ያልታወቀ ወይም ወድቆ የተገኘ (ለምሳሌ ገንዘብ)።

ተጣፋ ግ (ሂሳ.) ክፍልፋይ ቁጥር ያለቀሪ ሊያካፍል በሚችል ቁጥር ተከፋፈለ። ለምሳሌ 2/4 በሁለት ሲጣፋ ½ ይሆናል።

ተጠፋፋ ግ ሳይገናኝ ቀረ፣ ተጣጣ፣ አንዱ የሌላውን አድራሻ አጣ።

አጠፋ ግ 1. ረሳ፣ ዘነጋ (ያውቀው የነበረውን)። 2. አባከነ (ገንዘብን፣ ጊዜን፣...)። 3. ተሳሳተ፣ ትክክል ያልሆነ ድርጊት ፈፀመ። 4. ገደለ፤ ጨረሰ፣ አወደመ። *መድሃኒቱ ተባዮችን አጠፋቸው።* 5. አበላሸ፣ አጎደፈ፣ ጉዳት አደረሰ። 6. መጥፎ ጠባይን አስተማረ። 7. ከህግ፣ ከደንብ ውጭ የሆነ ነገር ፈፀመ። 8. አስወገደ፣ እንዳይኖር አደረገ። *ስራ ድህነትን አጠፋ።* 9. እንዳይታይ፣ እንዳይታወቅ፣ እንዳይሰማ አደረገ። *አድራሻውን አጠፋ።* 10. አንድ ነገር እንቅስቃሴውን፣ ስራውን እንዲያቆም አደረገ። *ሞተሩን አጠፋ /መብራቱን አጠፋ።*

አጥፊ ቅ 1. ወንጀለኛ። 2. ስህተተኛ፣ በደል ፈፃሚ። 3. ጠባየ ብልሹ፣ ስርአት የለሽ።

አጥፊና ጠፊ ገዳይና ሟች።

አጠፋፋ ግ 1. ደባበቀ፣ ሸፋፈነ (መረጃን)። 2. ጨረሰ፣ አባከነ (ገንዘብን)።

አጣፋ ግ ክፍልፋይ ቁጥሮችን ያለቀሪ ሊያካፍለው በሚችል ቁጥር አቃለለ፣ አካፈለ። (ለምሳሌ፣ 2/4 በሁለት ሲያጣፉት 1/2 ይሆናል)።

ጠፋ[2] ግ 1. በጥፊ መታ፣ አጮለ። 2. እንዝርትን ለማሽከርከር በጭን ላይ አፍተልትሎ አሾረ።

ጥፊ ስ 1. ውስጥ እጅ (ከመዳፍ እስከ ጣት ጫፍ ያለው የእጅ አካል)። 2. በውስጥ እጅ አማካይነት የሚደረግ ምት። 3. ከአይን ስር ያለው ቆዳ እብጠት በሽታ።

በጥፊ ከደነበት/ላሰው/ አላሰው/ መረገበት በጥፊ መታው።

ተጣፋ ግ ምች ወይም ሽውታ የታችኛውን የአይን ሽፋን አሳበጠ።

አጣፋ ግ 1. ጋቢን ወይም ኩታን ዘርግቶ በቀኝና በግራ ትከሻው ላይ ጣል በማድረግ ለበሰ። 2. በጥፊ መታ፣ አጮለ።

ጠፍ "**ጠፋ**[1]" ስር ተመ.

ጠፍር "**ጠፈረ**[1]" ስር ተመ.

ጠፍታ "**ጠፈፈ**" ስር ተመ.

ጠፍጣፋ "**ጠፈጠፈ**" ስር ተመ.

ጡ የ "**ጠ**" ፊደል ካእብ ዘር።

ጡሊ[1] ስ መንገደኛ ውሃ የሚይዝበት ቅል፣ ቅምጫና።

ጡሊ[2] "**ጡል**" ስር ተመ.

ጡል

ጡሊ ቅ ቀዥቃዣ፡ ዘዋሪ፥ ከውካዋ።

ጡል ጡል አለ ግ ወዲያ ወዲህ ተመላለሰ፥ ተንከወከወ፡ ተንቀዠቀዠ።

ጡረተኛ "**ጡረ**" ስር ተመ.

ጡረታ ዝ.ከ.

ጡር ስ ግፍ፡ በደል።

ጡር ሰራ በደለ፥ ግፍ ፈፀመ።

ጡር አለበት ግፍ ሰርቷል፥ በድሏል።

ጡረኛ ቅ ግፈኛ፡ በደለኛ።

ጡብ ስ ከሸክላ አፈር የሚሰራና አራት ማእዘንነት ያለው፡ ለግንብ መስሪያ የሚሆን ሸክላ።

ጡብ

ጡብ አለ ግ 1. ከላይ ወደ መሬት ዘሎ ወረደ፥ ዱብ አለ። 2. ዘለለ፡ እንጣጥ አለ።

ጡብ ጡብ አለ ግ ዱብ ዱብ፥ እንጣጥ እንጣጥ አለ፥ ዘለለ።

ጡት ስ 1. በሰው ደረት ወይም በእንስሳት ጉያ ላይ ተንጠልጥሎ የሚገኝ፥ ልጆቻቸው የሚመግቡትን ወተት የሚያመነጭ የሰውነት ክፍል (በወንዶች ላይ ያለው ግን ትንንሽ ከመሆኑም ሌላ ወተት አይወጣውም) (ስእሉን ሰውነት ስር ተመ.)። 2. በማንቆርቆሪያ፥ በኩስኩስት፥... ጎን በኩል ወጣ ብሎ የሚገኝ የፈሳሽ ማውረጃ ቀዳዳ።

ጡት ተጣባ የጡት ልጅና የጡት አባት ወይም እናት በመሆን ተዛመደ።

ጡት አጠባ የጡት ልጅ አደረገ።

ጡት ጠባ የአንድን ሰው በማር የተቀባ አውራ ጣት በጡት ምሳሌ በመጥባት ተዛመደ፥ ልጁ ሆነ።

ጡት ጣለ ጡት መጥባት ተወ።

የጡት ልጅ ስ ከትውልድ ሃረግ ውጭ የሆነና የአንድን ሰው በማር የተነከረ አውራ ጣት በመጥባት እንደ ልጅ ሆኖ የተዛመደ ሰው።

የጡት መያዣ ስ ሴቶች ጡታቸውን ደግፎ እንዲይዝላቸው የሚያደርጉበት፥ ብዙውን ጊዜ ማንገቻ ያለው አነስተኛ የጡት መደገፊያ ልብስ ።

የጡት አባት ስ የጡት ልጅ ለሚሆነው ሰው (ከትውልድ ሃረግ ውጭ ለሆነ) በማር የተነከረ ጣቱን በማጥባትና ቃል ኪዳን በመግባት እንደ አባት ሆኖ የተዛመደ ሰው።

የጡት እናት ስ የጡት ልጅ ለሚሆነው ሰው (ከትውልድ ሃረግ ውጭ ለሆነ)በማር የተነከረ ጣቷን በማጥባትና ቃል ኪዳን በመግባት እንደ እናት ሆና የተዛመደች ሴት።

ጡት አስጣይ ስ ተከታይ ታናሽ ወንድም ወይም እህት።

ጡንቻ ስ 1. የመለጠጥና የመጠመር ባህርይ ያለው፥ ከትከሻ እስከ ክርን ባለው የክንድ ክፍል ላይ የሚገኝ ፍርጥም ያለ ስጋ። 2. በሰውና በእንስሳት ሰውነት ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ላይ የሚገኝ፡ የመለጠጥና የመኮማተር እንዲሁም የመሰብሰብ ባህርይ ያለውና ለእንቅስቃሴ የሚያስፈልግ ጠንካራ ስጋ። 3. (ዘይ.) ሃይል፥ አቅም፥ ጉልበት። *ጡንቻውን ለካው።*

ጡንቻውን አዳበረ (ስፖ.) የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን በመስራት ጡንቻውን አዳበረ፥ አፈረጠመ።

ጡንቸኛ ቅ ሃይለኛ፥ ጉልበተኛ፥ ተደባዳቢ (ሰው)።

ጡን ጡን አለ "**ጠነጠነ**" ስር ተመ.

ጡዘት "**ጦዘ**" ስር ተመ.

ጡዝ

ጡዝ አደረገ ግ ፈሳ፥ አንዛረጠ።

ጡጥ

ጡጥ አለ ግ አነስና አጠር ያለ የፈስ ድምፅ ተሰማ ቁቅ አለ።

ጡጥ አደረገ ግ አነስና አጠር ያለ ድምፅ ያለው ፈስ ፈሳ።

ጡጥም ከፈስ ተቆጠረች በጣም ትንሽም ጉዳይ እንደ ትልቅ ቁም ነገር ታየች ወይም ተቆጠረች ለማለት የሚነገር።

ጡጦ ስ ህፃናት ወተት ወይም ሌላ ፈሳሽ የሚመገቡበት (እንደ ጡት የሚመጠምጡት ወይም የሚጠቡት) ከፕላስቲክ የሚሰራ ጠርሙስ መሰል እቃ ና በአፍ የሚጠጣው ጫፍ በአንድነት ወይም በተናጠል የሚጠሩበት ስም (የሚጠባው ጫፍ የጡጦ ጫፍም ይባላል)።

ጡጦ አይጠባም ህፃን አይደለም፥ አይታለልም።

ጡጫ ስ የታጠፈ ወይም የተጨበጠ የእጅ ጣት፥ ቡጢ።

ጡጫ ሆድ ስ የተወጠረ ወይም የተቆዘረ ሆድ።

ጢ የ "**ጠ**" ፊደል ሳልስ ዘር።

ጢል

ጢሎሽ ስ የዛፍን ቅርንጫፍ በማዝመም ወይም ገመድን እንጨት ላይ በማሰርና በላዩ ላይ በመንጠልጠል እየተወዛወዙ የሚጫወቱት እንደ ጅዋጅዌ ያለ የልጆች ጨዋታ።

ጢል አለ ግ ተንጠለጠለ፥ ተሰቀለ።

ጢም "**ጺም**"ን ተመ.

ጢም̈ አለ ግ በጣም ሞላ።

ጢር አለ ግ ከራ፥ ቃበየ፥ ተጀነነ።

ጢራ ቅ ኩሩ፥ ጅንን።

ጢሰኛ "ጪሰ" ስር "ጪሰኛ"ን ተመ.

ጢስ "ጪሰ" ስር "ጪስ"ን ተመ.

ጢሻ "ጥሻ"ን ተመ.

ጢቅ^1

ጢቅ አለ ግ ሞላ፥ ጢም አለ።

ጢቅ አደረገ ግ ሞላ፥ በብዛት ከተተ፥ ጠቀጠቀ (ሻንጣን፥..)።

ጢቅ^2

ጢቅታ ስ አፈናጥረው የተፉት ምራቅ።

ጢቅ አለ ግ 1. ምራቁን በጥርሶቹ መካከል አፈናጥሮ ተፋ። 2. (ዘይ.) ተፀየፈ፥ አጥላላ።

ጢብኛ "ጥብኛ" ን ተመ.

ጢን

ጢን አለ ግ 1. ሞላ፥ ጢም አለ። 2. (ዘይ.) ከራ፥ ተንቀባረረ። 3. (ዘይ.) በጣም ሰከረ።

ጢንጦ ስ ከሌሎች ጋር በመካፈል የሚገኝ አነስተኛ መሬት።

ጢው

ጢው አለ ግ ጮሀ፥ ጡጥ አለ (ፈስ)።

ጣ^1 የ "ጠ" ፊደል ራብእ ዘር።

ጣ^2

ጣ አለ ግ እሳት ሲነድ ወይም ሲፈናጠር የሚያሰማውን አይነት ድምፅ ሰጠ ወይም አሰማ።

ጣለ ግ 1. ወረወረ፥ አሽቀንጠረ። 2. ደበለለ፥ ዘረረ (በትግል) ። 3. እንዲወድቅ፥ እንዲጠፋ አደረገ። *ብር ጣለ።* 4. ገነደሰ፥ ከስሩ ቆረጠ (ዛፍን)። 5. መገልገል፥ መጠቀም ተወ (አንድን እቃ)። 6. አእምሮውን ስቶ እንዲወድቅ አደረገ (ብዙውን ጊዜ የአእምሮ ህመም)። 7. ከፈለ (የእቁብ መዋጮውን)።8. መታ፥ ገደለ ወይም አቆሰለ (በመሳሪያ)። 9. በርካሽ ሸጠ። 10. እንዳያልፍ አደረገ (በፈተና)። 11. ተወ። *ሰውዬውን ጥሎ ሄደ።* 12. ወሰነ፥ መደበ። *መቀጫ ጣለ።* 13. (የን.አነ.) ሰጠ።*በየወሩ ትንሽ ገንዘብ ይጥልለታል።*

በ ___ ላይ ጣለ በ ___ ላይ አሳረፈ። *ሃላፊነቱን በእሱ ላይ ጣለ።*

ጣለበት 1. አይኑን ጋረደው፥ ከለለው፥እንደልብ ማየት ተሳነው፥(በበሽታ ምክንያት)። 2. አዘዘበት፥ ፈረደበት።

ጣል አደረገ ግ ተወት አደረገ፥ ቸላ አለ።

ጣል ጣል አደረገ ግ አራከሰ፥ አዋደቀ፥ አጣጣለ።

ጥሎ ማለፍ ስ (ስፖ.) በተለያዩ ብዙ ቡድኖች መካከል በሚደረግ የእግር ኳስ ወይም ሌላ ውድድር ላይ ተሸናፊው ቡድን እየወጣና አሸናፊው ቡድን ወደሚቀጥለው ደረጃ እያለፈ ቀሪዎቹ የሚጋጠሙበት የውድድር ሂደት።

መጣያ ስ ሚዛኑን ለማስተካከል በጭነት ላይ የሚጨመር ትንሽ ነገር።

ጣጣለ ግ ተወ።

ጣጥሎ ሄደ ግ ትቶ ሄደ (እቃውን፥ ንብረቱን፥ቤቱን፥...)።

ጥለት ስ 1. በፊት ላይ የሚወጣና ፊትን የሚያጠቁር ማዲያት። 2. (ዘይ.) የእግዚአብሄር ቁጣ፥ መአት።

ጥሎሽ ስ በጋብቻ ስነስርአት ላይ ከሙሽራው ለሙሽራዋ የሚሰጥ ገፀበረከት፥ ስጦታ።

ተጣለ ግ ተተወ፥ ከጥቅም ውጭ ሆኖ ወደቀ።

አጣጣለ ግ አዋደቀ፥ አራከሰ።

አጣጣል ስ አፃፃፍ (የፊደል)።

አስጣለ ግ 1. አዳነ፥ አተረፈ (ከአደጋ፥ ከጉዳት፥..)። 2.አስተወ።

ጣሊቃ "ጠለቀ^1" ስር ተመ.

ጣመ ግ 1. ጣፈጠ፥ ጥሩ ጣእም ኖረው (ምግብ፥ መጠጥ፥...)። 2. ደስ አሰኘ፥ አረካ (ንግግር፥ ፅሁፍ፥ ስራ ፥...)። *ንግግሩ ጣመኝ።*

ጣእም ስ 1. የአንድ ነገር የጣፋጭነቱ ወይም የመራራነቱ ስሜት።*ጣእሙን አልቀመስኩትም።* 2. ጣፋጭነት።*ጣእም አለው።*3.ዋጋ፥ ጠቀሜታ፥ ጥሩነት። *የእናት አባት ጣእም/ የገንዘብ ጣእም።* 4. አስደሳችነት፥ ውበት።

ጣእም አጣ 1. አልጣፍጥ አለ። 2. ለዛ አጣ፥ አስጠላ፥ ቸከ።

ጣእመ ቢስ ቅ ለዛ የሌለው፥ የማያስደስት።

ጣእመ ዜማ ስ የሚስብ ወይም የሚያስደስት የዜማ ቃና ።

ተጣጣመ ግ ተስማማ፥ ተዋደደ፥ አብሮ የሚሄድ ሆነ።

የማይጣጣም የማይስማማ፥ አብሮ የማይሄድ።

አጣጣመ ግ 1. ጣእምን ለመለየት በምላሱ ፈተሸ፥ ቀመሰ ። 2. አብላላ፥ ተገነዘበ (ነገርን)። 3. አስማማ፥ አብሮ እንዲሄድ አደረገ። 4. አደነቀ። *ስነፅሁፍን የማጣጣም ችሎታ አለው።*

ጣመነ ግ ደከመ፥ ጓጎለ (ሰውነት)።

ጣመን ስ ከጉዞ ወይም ከጉልበት ስራ የሚመጣ ድካም፥ የሰውነት መጓጎል።

ጣማ

ጣማ ገንዘብ በገዛ ራስ ድካም፥ በልፋት የተገኘ የሃቅ ገንዘብ።

ጣምራ "*ጠመረ" ስር ተመ.

ጣረ ግ ተጣጣረ።

ጥረት ስ ልፋት፥ ትጋት፥ ድካም (አንድ ነገር ለማግኘት፥ ለመስራት፥...)።

ተጣጣረ ግ ለፋ፥ ደከመ፥ ታገለ፥ ብርቱ ሙከራ አደረገ (ከአላማ ለመድረስ)።

***ጣረ**

ጣር(ፃእር) ስ 1.'ጭንቀት፥ ስቃይ።2.ነፍስና ስጋ በሚለያዩበት ጊዜ የሚሰማ ፅኑ የሆነ የህመም ስሜትና ስቃይ።

ጣር በዛበት በጣም ተሰቃየ፤ ነፍሱ ከስጋው በቶሎ አልለይ አለች።

ጣረ ሞት (ፃእረ ሞት) ስ አለልክ ቀጭንና አስጠሊታ፥ ጭጋጋ የሆነ ገፅታ።

ጣረ ሞት (ፃእረ ሞት) ይዞታል እያጣጣረ ነው።

አጣጣረ ግ ጣር ላይ ሆነ፤ ሊሞት ደረሰ።

ጣራ (ጣሪያ) ስ 1. ከግድግዳ በላይ ያለ የቤት መዋቅር፥ ባጥ፥ ክዳን።2. የከፍታ መጠን። *የደመወዙ ጣሪያ አምስት መቶ ብር ነው።*

ጣር "*ጣረ" ስር ተመ.

ጣስ ግ 1. ሰበረ፥ አፈረሰ። 2. በሃይል አለፈ፥ ገፍቶ አልፎ ሄደ። 3. ተላለፈ፥ አፈረሰ (ህግን፥ ስርአትን...)። 4. ጎፈሬ የነበረውን ፀጉር ሹርባ ሰራ። 5. ፈጨ (አሻሮን)።

ተጣሰ ግ ፈረሰ፥ ሳይከበር ቀረ (ህግ)።

ጣሰሰ ግ ለሸለሸ፥ አጋደመ (ሜካን)።

ጣሳ ስ ከቆርቆሮ የሚሰራና ለመያዣ፥ ለመጥለቂያ፥ ለመስፈሪያ የሚያገለግል የቤት እቃ ወይም ቁሳቁስ።

ጣቃ ስ ያልተሰፋ፥ ትልቅና ጥቅል የሆነ ብትን ጨርቅ።

ጣቢያ ስ 1. የአንድ ተግባር ማከናወኛ ቦታ ወይም መስሪያ ቤት። *የምርምር ጣቢያ /የእርሻ ጣቢያ።* 2. ፖሊስ ስር "ፖሊስ ጣቢያ"ን ተመ.

ጣባ ስ ቅርፁ ጎድጓዳ ሳህን የመሰለና ከሸክላ ወይም ከእንጨት የሚሰራ የቤት እቃ (ስእሉን የ"ሸክላ እቃ" ስር ተመ.)።

ጣብቂያ "*ጠበቀ^{1}" ስር ተመ.

ጣት ስ በእጅና በእግር ጫፍ ላይ የሚገኝና አንጓ ያለው ተንቀሳቃሽ የሰውነት ክፍል።

ጣቱን ቀሰረበት ዛተበት፥ በተቃዋሚነት ወይም በጠላትነት ተነሳበት።

ጣቱን ይጠባል እንዴ! እንደ ህፃን ይታለላል ወይ!

የጣት ቤዛ ስ ልብስ የሚሰፋ ወይም የሚዘመዝም ሰው መርፌው ጣቱን እንዳይወጋው በሌባ ጣቱ ላይ የሚሰካው መከላከያ 1 ከስቱባን።

የጣት ወርቅ ስ ከወርቅ የተሰራና በእጅ ጣት ላይ የሚደረግ ጌጥ።

የጣት ውሃ ስ ለእጅ መታጠቢያ የሚቀርብ ውሃ።

የጣት ፊርማ ስ ጣትን ቀለም በማስነካትና አሻራን በወረቀት ላይ በማሳረፍ የሚፈረም ፊርማ።

ጣእም "ጥዑም" ስር ተመ.

ጣእት ስ ሰዎች እንደ አምላክ የሚያመልኩበት ድንጋይ፥ ዛፍ ወይም ከድንጋይ፥ ከእንጨት፥... የሚሰራ ምስል።

ጣውላ ስ 1. ተሰንጥቆ የተላገ እንጨት። 2. ከተላገ እንጨት የተሰራ የቤት ወለል።

ጣውንት ስ ጎባን፤(አንዲት ሴትን በተለያየ ጊዜ ያገቡ ወንዶች ወይም አንድን ወንድ በተለያየ ጊዜ ያገቡ ሴቶች እርስ በርሳቸው ያላቸው ግንኙነት መጠሪያ)።

ጣዎስ ስ ጅራቱ የሚብለጨለጭ፥ አንገቱና ራሱ ሰማያዊ መልክ ያለው ተለቅ ያለ ወፍ፤ ኦፌ ገንትም ይባላል። (ስእሉን "ወፍ" ስር ተመ.)

ጣዝማ ስ ከንብ አነስ ከትንኝ ከፍ የምትልና ማሯን በመሬት ውስጥ የምትጋግር የነፍሳት አይነት።

ጣዝሙት (ዘይ.) ልባም፥ ባለሙያ (ሴት)።

ጣዝማ ማር ስ ጣዝማ የምትሰራው ወለላ ማር።

ጣደ ግ ለማብሰል፥ ለመቀቀል ወይም ለማፍላት እሳት ላይ ወይም እሳት ያለበት ምድጃ ላይ አስቀመጠ (ምጣድን፥ ድስትን፥...)።

ጥዶ ዘለል ቅ 1. ከውካዋ፥ ወፈፌ። 2. የጣደችውን ሳታወጣ ወይም ስራው ሳያልቅ ትታው ወሬ ፍለጋ የምትዞር።

ምጣድ ስ ከሸክላ ወይም ከብረት የሚሰራ ለእንጀራ፥ ለዳቦ፥ ለቂጣ፥..ማብሰያ የሚያገለግል ጠፍጣፋና ክብ የሆነ የቤት እቃ።

የምጣድ ሽሮ ስ ሽሮን ከዘይትና ከሌሎች ቅመሞች ጋር አዋህዶ በምጣድ በማብሰል የሚዘጋጅ እንደ ወጥ የሚያገለግል የእንጀራ ማባያ።

ተጣደ ግ 1. እሳት ላይ ተደረገ(ድስት፥ ምጣድ፥...)።2. እሳት ዳር ተቀመጠ፥ ተወዘፈ (ሰው)።

ጣዲቅ "ፀደቀ" ስር "ፀዲቅ"ን ተመ.

ጣጋ ቅ ክሲታ፥ ኩሳሳ።

ጣጣ ስ 1. ችግር፣ ውጣውረድ፣ ውስብስብነት። 2. መዘዝ።

ጣጣ ገባ መከራ፣ ችግር ውስጥ ገባ።

ጣጠኛ ቅ መከራው፣ ችግሩ የበዛ። 2. መዘዘኛ።

***ጣጣ**

ጣጣቴ ስ 1. ከህመም ያድናል እየተባለ በሽተኛን በጋለ ብረት የመተኮስ ድርጊት። 2. ለፍላፊ። 3. የሚንጣጣ ድምፅ።

ተንጣጣ ግ 1.እየተቆላ ያለ ተልባ ወይም ማሽላ የሚያሰማውን አይነት ድምፅ አሰማ። 2. ለፈለፈ።

አንጣጣ ግ 1. የሚንጣጣ ተከታታይ ድምፅ አሰማ ወይም እንዲሰማ አደረገ። 2.አስለፈለፈ፣ አስቀባጠረ።

ጣጣለ "ጣለ" ስር ተመ.

ጣጣቴ "*ጣጣ" ስር ተመ.

ጣፈ ግ በተቀደደው ልብስ ላይ ሌላ ጨርቅ ደርቦ ሰፋ፣ ጠቀመ፣ ደረተ። 2. አላከከ። *ጥፋቱን በእኔ ላይ ጣፈብኝ።*

መጣፊያ ስ በተቀደደ ጨርቅ ላይ ተለጥፎ የሚሰፋ እራፊ ወይም ቁራጭ ጨርቅ።

ተጣፈ ግ ተደረተ፣ ቀዳዳው እራፊ ጨርቅ ተደርቦበት ተሰፋ።

ጣፈጠ ግ ጣመ፣ ጥሩ ጣእም አገኘ (ምግብ፣ መጠጥ)።

ጣፋጭ ቅ 1. የሚጥም፣ ጥሩ ጣእም ያለው፣ የሚጣፍጥ። 2. በኳርነት ያለው።

አጣፈጠ ግ 1. አጣመ፣ ጥሩ ጣእም እንዲኖረው አደረገ (ምግብን፣ መጠጥን)። 2. አሳመረ፣ አስዋበ (ነገርን)።

ማጣፈጫ ስ (ምግብን፣ መጠጥን) የሚያጣፍጥ፣ ጥሩ ጣእም እንዲሰጥ የሚያደርግ ቅመም ወይም ሌላ ነገር።

ጣፊያ ስ በሆድ ውስጥ በግራ በኩል በላይኛው ክፍል የሚገኝ፣ ጠቆር ያለ ቀይ መልክና ሞላል ያለ ቅርፅ ያለው፣ ደምን በመስራት ለማጠራቀምና ለማጣራት የሚጠቅም የሰውነት ክፍል።

ጣፋ ስ ከወርቅ፣ ከብር፣... የሚሰራ የጋሻ ጌጥ።

ጣፋጭ "ጣፈጠ" ስር ተመ.

ጣፎርዴ ቅ (ስድብ) ጋጠወጥ፣ ባለጌ።

ጤ የ "ጠ" ፊደል ሃምስ ዘር።

ጤስ "ጨስ" ን ተመ.

ጤቅ ስ ድብዳብ፣ መደላድል (ጭነቱ እንዳይጎዳው በጋማ ከብት ጀርባ ላይ የሚደረግ)።

***ጤነ**

ተጤነ ግ ተመረመረ፣ ልብ ተባለ፣ ተስተዋለ።

አጤነ ግ መረመረ፣ አስተዋለ፣ ልብ አደረገ።

ጤና ስ ደህንነት፣ ከበሽታ ነፃ መሆን።

ጤና ሰጠ ሰላም ሰጠ።

ጤና ነሳው 1. ሰላም እንዳያገኝ አደረገው፣ አወከው። 2. ህመምተኛ ወይም ታማሚ ሆነ።

ጤና አገኘ ታሞ የነበረው ዳነ፣ ጤነኛ ሆነ።

ጤና ይስጥልኝ ሰዎች በሚገናኙበት አንዳንዴም በሚለያዩበት ጊዜ የሚለዋወጡት የሰላምታ ቃል።

ጤና መኮንን ስ በህክምና ትምህርት የሰለጠነ ባለሙያ።

[የ]ጤና ረዳት ስ የተወሰነ የህክምና እርዳታ አሰጣጥ ትምህርት የተማረ የጤና ባለሙያ።

ጤና ቢስ ቅ 1. አዘውትሮ የሚያመው፣ በሽተኛ። 2. ነገረኛ፣ ጠበኛ።

ጤና ጣቢያ ስ ደረጃው ከሆስፒታል አነስ የሚልና መለስተኛ የህክምና እርዳታ የሚሰጥበት የህክምና ተቋም።

ጤነኛ ቅ 1. የማያመው፣ ህመም የሌለው። ጤናማም ይባላል።2. እንከን፣ ችግር፣... የሌለበት።

ጤናማ "ጤነኛ"ን ተመ.

ጤናዳም(ጤና አዳም) ስ ከአገር ባህል መድሃኒት ጋር እየተቀመመ ወይም ብቻውን ለመድሃኒትነት ያገለግላል የሚባልና ጥሩ ሽታ ያለው ተክል።

ጤንነት ስ ደህንነት፣ የሰውነት፣ የአካል ጤናማ መሆን።

ጤዛ ስ በሳርና በቅጠል ላይ ጧት ጧት ወይም ዝናብ ከዘነበ በ ኋላ ተንቆርዞ የሚታይ የውሃ ጠብታ።

ጤዛ ጣለ በሳርና በቅጠል ላይ የውሃ ጠብታ ተንቆረዘዘ።

ጤዛ ረገፈ ጤዛው ደረቀ።

ጤፍ ስ ተፈጭቶና በቀጭኑ ተቦክቶ ሲጋገር እንጀራ የሚሆን ትናንሽ ፍሬዎች ያሉት የእህል አይነት፤ ፍሬውም ጤፍ ይባላል።

ጥ የ "ጠ" ፊደል ሳድስ ዘር።

ጥለት^{1} ስ በነጠላ፣ በቀሚስ፣ በጋቢ፣... ዳር ላይ የሚሰራ፣ የተለያየ ቀለም ያለው ክር፤ እዳይት።

ጥለት ጣለ በሸማ፣ በኩታ፣... ዳር ላይ ጥለት ሰራ፤ በጥለት አስጌጠ።

ጥለት^{2} "ጣለ" ስር ተመ.

ጥሰኛ "ጠሳ²" ስር ተመ.

ጥሳ "*ጠሳ" ስር ተመ.

ጥሳሽት(ጠለሽት፥ ጥሳት) ስ በእሳት ጢስ ምክንያት የሚፈጠር ጥቁር ቆሻሻ፥ ጥቀርሻ።

ጥሳሽት ለበሰ ፈቱ በጣም ጠቆረ (በሃዘን፥ በፀሃይ፥ በድንጋጤ፥... የተነሳ)።

ጥሳሽት ቀባ ስም አጠፋ ፤ አዋረደ።

ጥሳቻ "ጠሳ²" ስር ተመ.

ጥሳይ "ጠለለ" ስር ተመ.

ጥል "ጠላ²" ስር ተመ.

ጥልማሞት "ፅልሙት" ስር "ፅልማሞት"ን ተመ.

ጥልምያኮስ"ፅልመት"ስር "ፅልመያኮስ"ን ተመ.

ጥልቀት "ጠለቀ¹ " ስር ተመ.

ጥልቅ ዝ.ከ.

ጥልቆ ስ አነስተኛ መጥረቢያ።

ጥልባል ስ ከቄጠማ የሚሰራ የቤት ወለል ምንጣፍ።

ጥልፊያ "ጠለፈ" ስር ተመ.

ጥልፍ ዝ.ከ.

ጥልፍልፍ ዝ.ከ.

ጥሎሽ "ጣለ" ስር ተመ.

ጥመት " ጠመመ" ስር ተመ.

ጥሙር "ጠሞረ" ስር ተመ.

ጥማት "ጠማ" ስር ተመ.

ጥማድ "ጠመደ¹" ስር ተመ.

ጥም "ጠማ" ስር "ጥማት"ን ተመ.

ጥምልምል "*ጠመለመለ" ስር ተመ.

ጥምር "*ጠመረ" ስር ተመ.

ጥምቀት "ጠመቀ" ስር ተመ.

ጥምቢራ (ጥንቢራ)

ጥምቢራው ዞረ'ል በጣም ሰከረ'ል።

ጥምብ "ጠነባ" ስር ተመ.

ጥምዝ "ጠመዘዘ" ስር ተመ.

ጥምጣም "ጠመጠመ" ስር ተመ.

ጥምጥም ዝ.ከ.

ጥሞና "ፅሞና"ን ተመ.

ጥረሾ ስ ሳይበነ (ኩፍ ሳይል) የሚጋገር ስስና ደረቅ የሆነ የገብስ ቂጣ።

ጥረት "ጣረ" ስር ተመ.

ጥሩ "ጠራ²" ስር ተመ.

ጥሩምባ ስ 1. ከነሃስ ወይም ከሌላ ተመሳሳይ ነገር የሚሰራ፥ ከፍ ያለ ድምፅ የሚያወጣና በትንፋሽ የሚሰራ የሙዚቃ መሳሪያ (ስእሉን የሙዚቃ መሳሪያ ስር ተመ.)። 2. የመኪና ጥሩምባ።3. (ዘይ.) ወሬኛ፥ ለፍላፊ።

ጥሩምባ ነፊ ስ ጥሩምባን በመጠቀም የሙዚቃ ድምፅ የሚያሰማ ወይም የጥሪ መልእክት የሚያስተላልፍ ሰው።

ጥሩር ስ በቀድሞ ጊዜ ወታደሮች ጦርነት ላይ ሲሰማሩ ለመከላከያነት የሚለብሱት ከብረት የሚሰራ የጦር ልብስ።

ጥሩር

ጥሪ "ጠራ¹" ስር ተመ.

ጥሪት ስ አንጡራ ሃብት፥ ንብረት።

ጥራር ስ ከሸንበቆ ወይም ከቀርከሃ ወይም ከሃረግ፥... የሚሰራ አገልግል፥ መሶብ፥ ቅረጫት።

ጥራቢ "ጠረበ" ስር ተመ.

ጥራት "ጠራ²" ስር ተመ.

ጥራዝ "ጠረዘ" ስር ተመ.

ጥራጊ "ጠረገ" ስር ተመ.

ጥሬ ስ 1. ያልላመ፥ ያልደቀቀ፥ ያልተፈጨ እህል። 2. ያልበሰለ፡ ያልሞከከ፥ ያልነመረ (ፍራፍሬ)። 3. ቆሎ፥ ንፍሮ። *የቆሎ ተማሪ ጥሬ በልቶ፥ ውሃ ጠጥቶ ነው የሚማረው።* 4.በእሳት ያልበሰለ ወይም ያልተቀቀለ (እህል፥ ስጋ)። 5. (ዘይ.) ነፍስ ያላወቀ፡ ማስተዋል የሚያንሰው።6. ከሚፈለገው ደረጃ ያልደረሰ፥ ገና የሆነ።*ጉዳዩ ገና ጥሬ ነው።*

ጥሬ ነው 1. አልተጎዳም፡ አላለቀም (ልብስ)። 2. አልበሰለም፥ ለመበላት አልደረሰም። 3. አልሰለጠነም(ለሰው)።

ጥሬ ስጋውን በላት አሙት።

ጥሬና ብስል ቅ የጥሩና የመጥፎ፥ የሚረባና የማይረባ ነገር ቅልቅል።

ጥራጥሬ ስ እንደ ባቄላ፥ አተር፥ምስር፥... ያለ የእህል አይነት የወል መጠሪያ።

ጥሬ ካብ ስ ጭቃ፡ ኖራ፥ ስሚንቶ ያልገባበት፥ በድንጋይ ብቻ የተሰራ ካብ።

ጥሬ ዘር ስ (ሰዋ.) ከግሳዊ ቃል በእርባታ ዘዴ የሚፈጠርና በስምነት ሊያገለግል የሚችል ውልድ ቃል (ለምሳሌ መነነ ብሎ ምናኔ፤ ሰቀለ ብሎ መስቀል፤ ለፋ ብሎ ልፋት፤ ዳነ ብሎ መድሃኒት፥... የመሳሰለው ሁሉ)።

ጥሬ ገንዘብ ስ ብር ብቻ (እቃን ወይም ሌላ ንብረትን ሳይጨምር)።

ጥሬ ጥጥ ስ ያልተፈለቀቀ ወይም ፍሬው ያልወጣ ጥጥ።

ጥሬ ጨው ስ ያልተፈጨ ጨው፤ አሸቦ።

ጥሬ ፊጅ ስ ቡኒ መልክ ያለውና ብዙ ሆና ባንድነት የሚሄድ፥ እህል የሚበላ የወፍ አይነት፤ ጨረባ።

ጥር ስ ከታህሳስ ቀጥሎ የሚመጣ የአመቱ አምስተኛ ወር ስም።



ጥርስ

ጥርስ ስ 1. በሰውና በእንስሳት አፍ ውስጥ የሚገኝ፥ ለምግብ መፍጫ የሚያገለግል፥ ነጭና ጠንካራ የሆነ የሰውነት ክፍል። 2. የማጭድ ወይም የመጋዝ ዘርዛራ የሆነው ስለት። 3. እባጭ ወይም ብጉንጅ በሚፈርጥበት ጊዜ ከውስጡ የሚወጣ ጠጣር ያለ መግል። 4. እንቅስቃሴን ከአንድ አካል ወደ ሌላ ለማስተላለፍ፥ ፍጥነትን ለመቆጣጠር፥ አቅጣጫን ለመቀያየር፥... የሚያገለግልና በዘርዛራው የተከረከረ ጠርዝ ያለው የሞተር ወይም የማሽን፥... ክፍል።

በጥርሱ ሸኘ በፈገግታ ደለለ፥ አታለለ፥ ሸንገለ።

ጥርሱ ረገፈ ጥርሱ ወለቀ (ብዙውን ጊዜ ከአንድ በላይ ጥርስ)።

ጥርሱን ቆረጠመ ጥርሱን አፋጨ፤ አንቀራጨጨ (በእንቅልፍ ጊዜ)።

ጥርሱን ሸርፏል/ ሰብሯል እድሜው ከፍ በማለቱ በፊት የነበረው ጥርስ ወልቆ ሌላ አብቅሏል (እንደ በቅሎ፥ ፈረስ፥... ያለ እንስሳ)።

ጥርስ አወጣ 1. ጥርስ አበቀለ። 2. ሳለ፥ ሞረደ (መጋዝን፥ ማጭድን፥...)።

ጥርሱን ነከሰ ዛተ፥ ቂም ያዘ።

ጥርስ ገባ ተጠላ፥ ተጠመደ።

የጥርስ ሃኪም ስ በተለይ በጥርስ ህክምና የሰለጠነ ባለሙያ።

የጥርስ ሳሙና ስ ጥርስን ለማፅዳት የሚያገለግል ሳሙና።

የጥርስ ብሩሽ ስ ጥርስን ለማፅዳት የሚያገለግል ብሩሽ።

ጥርሰ በረዶ ቅ ጥርሱ በጣም ነጭ የሆነ።

ጥርሰ ፍንጭት ቅ በፊት ጥርሶቹ መካከል ክፍት ቦታ ያለው፤ ፍንጭትም ይባላል።

ጥርሳም ቅ 1. ጥርሱ ወደ ውጭ የወጣ፤ ገጣጣ። 2. መሳቅ የሚያበዛ።

ጥርቃሞ "*ጠረቀመ" ስር ተመ.

ጥርቅም ዝ.ከ.

ጥርቅምቅም ዝ.ከ.

ጥርብ "ጠረበ" ስር ተመ.

ጥርኝ[1] ስ ገላዋ ዝባድ በመባል የሚታወቀውንና ጥሩ መአዛ ያለውን ኩስ መሳይ ወዝ የሚያመነጭ እንደ ድመት ያለች የአውሬ አይነት፤ ከአካሏ የሚመነጨውም ኩስ መሳይ ወዝ ጥርኝ ወይም ዝባድ ተብሎ ይጠራል (ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።

ጥርኝ ፈረስ ስ መልኩ ግራጫ የሆነ ፈረስ።

ጥርኝ[2] ቅ የእፍኝ ግማሽ፤ በአንድ የውስጥ እጅ ሊያዝ የሚችል መጠን። ላንድ ጥርኝ ቆሎ።

ጥርዝ "ጠረዘ" ስር ተመ.

ጥርጊያ "ጠረገ" ስር ተመ.

ጥርጣሪ "ጠረጠረ[2]" ስር ተመ.

ጥርጣሬ "ጠረጠረ[1]" ስር ተመ.

ጥርጥር ዝ.ከ.

ጥርጥስ " ጠረጠሰ" ስር ተመ.

ጥስቅ "ጠሰቀ" ስር ተመ.

ጥሻ(ጢሻ) ስ ጳዋ፤ ጥቅጥቅ ያለ ሳርና ቁጥቋጦ።

ጥቀርሻ ስ ጪስ በሚጨስበት ቤት ጣሪያ ወይም ኮርኒስ ላይ የሚገኝ የጪስ ብናኝ ጥርቅም፤ ጥላሸት።

ጥቁራት "ጠቆረ" ስር ተመ.

ጥቁሬ ዝ.ከ.

ጥቁር ዝ.ከ.

ጥቂት ቅ በጣም ትንሽ፤ መጠኑ ወይም ቁጥሩ አነስተኛ የሆነ።

ጥቃተኛ "*ጠቃ" ስር ተመ.

ጥቃት ዝ.ከ.

ጥቅለላ "ጠቀለለ" ስር ተመ.

ጥቅል ዝ.ከ.

ጥቅም "ጠቀመ" ስር ተመ.

ጥቅምት ስ ከመስከረም ቀጥሎ የሚመጣ የአመቱ ሁለተኛ ወር ስም።

ጥቅስ "ጠቀሰ" ስር ተመ.

ጥቅሻ ዝ.ከ.

ጥቅጥቅ "ጠቀጠቀ" ስር ተመ.

ጥቆማ "ጠቆመ" ስር ተመ.

ጥበቃ "ጠበቀ[1]" ስር ተመ.

ጥበበኛ "*ጠበበ" ስር ተመ.

ጥበብ ዝ.ከ.

ጥበት "ጠበበ" ስር ተመ.

ጥቢ "ጠባ[2]" ስር ተመ.

ጥቢኛ(ጢብኛ) ስ ሙልሙል ዳቦ፣ ህብስት።

ጥባት "ጠባ^2" ስር ተመ.

ጥብርር "*ጠበረረ" ስር "ጠብራራ"ን ተመ.

ጥብስ "ጠበሰ" ስር ተመ.

ጥብቅ^1 "ጠበቀ^2" ስር ተመ.

ጥብቅ^2 "ጠበቀ^1" ስር ተመ.

ጥብቅና "*ጠበቀ^2" ስር ተመ.

ጥብቆ ስ ጠበብ ብሎ የተሰፋ የልጅ ልብስ።

ጥብጣባ "ጠበጠበ" ስር ተመ.

ጥብጣብ ስ 1. ከፈትል ወይም ከተለያየ ጥለት ተጎንጉኖ የሚሰራ የስራ መታጠቂያ፣ ሽምቀቆ። 2. በካባ ላይ በስተፊት በኩል በግራና በቀኝ የሚወርድ ጌጥ 3. እንደ መቀነት ያለ ቀጭንና ረጅም ጨርቅ። *ሉዲሉ መንገድ በተመረቀ ጊዜ ጥብጣቡን የቆረጡት ስራ አስኪያጁ ናቸው።*

ጥብጥባት "ጠበጠበ" ስር ተመ.

ጥኑ "ጠና" ስር "ፅኑ"ን ተመ.

ጥና "ፅንሃህ" ን ተመ.

ጥናት^1 "ጠና" ስር "ፅናት"ን ተመ.

ጥናት^2 "*ጠና" ስር ተመ.

ጥንሰስ "ጠነሰሰ^1" ስር ተመ.

ጥንቁቅ "ጠነቀቀ" ስር "ጠንቃቃ"ን ተመ.

ጥንቃቄ "ጠነቀቀ" ስር ተመ.

ጥንቅሽ ስ 1. መልኩ እንደ በቆሎ አገዳ ያለ ሆኖ ቀጠን ቀጠን የሚል ሸንኮራ፤ ጥንቅሽ አገዳ። 2. አገዳው እንደ ሸንኮራ ጣፋጭነት ያለው የማሽላ ኣይነት።

ጥንቆላ "ጠነቆለ" ስር ተመ.

ጥንቢራ "ጥምቢራ"ን ተመ.

ጥንባት "ጠነባ" ስር ተመ.

ጥንብ ዝ.ክ.

ጥንታዊ "ጥንት" ስር ተመ.

ጥንት ተው.ግ ድሮ፤ ቀድሞ።

ጥንተ አካል ስ በቀድሞ ዘመን ወይም ከረጅም ጊዜ በፊት የነበረ የሰው ወይም የአውሬ ወይም የሌላ ነገር አካል ክፍል፤ ቅሪት።

ጥንታዊ ቅ የድሮ፣ በቀድሞ ዘመን የነበረ ወይም ከድሮ፣ ከጥንት ጀምሮ የነበረ፤ ያለ።

ጥንቸል ስ የፍየል ግልገል የምታክል፣ ስትሄድ ጡብ ጡብ እያለች የምትዘል፤ አጭር ጅራትና ረጅም ጆሮ ያላት እንስሳ(ስእሉን የዱር እንስሳ ስርጅ።

ጥንካሬ "ጠነከረ" ስር ተመ.

ጥንዚዛ ስ ሲበር ጥዝ ጥዝ የሚል ድምፅ የሚያሰማና ጥቁር ወይም አረንጓዴ የሆነ በራሪ ነፍሳት።

ጥንዚዛ

ጥንዚዛ የመሰለ በጣም ጥቁር የሆነ።

ጥንጒት "ጥንጁት" ን ተመ.

ጥንድ ቅ ሁለት፣ መንታነት ያለው።

በጥንድ በጥንድ ሁለት ሁለት በመሆን።

ጥንድ በሬ በአንድነት እርሻ ላይ የሚሰማሩ፣ የተቀናጁ ሁለት በሬዎች።

ጥንድ ጫማ አንድ ላይ የሚደረግ የሁለት እግር ጫማ።

ጥንጁት (ጥንጒት) ስ በወይና ደጋና በቆላ የሚበቅል፣ መልኩ ነጣ ያለ ሆኖ እሾህ ያለው፤ ለጠላ እቃ ማጠኛ፣... የሚያገለግል የእፅዋት ኣይነት።

ጥንግ "*ጠነገ" ስር ተመ.

ጥንጣን "ጠነጠነ^2" ስር ተመ.

ጥንጥን "*ጠነጠነ" ስር ተመ.

ጥንፍ "ጠነፈ" ስር ተመ.

ጥዋ "ፅዋ"ን ተመ.

ጥዋት "ጧት"ን ተመ.

ጥውር "ጦረ" ስር ተመ.

ጥዝ

ጥዝ አለ ግ ንብ ወይም ጥንዚዛ ሲበሩ የሚያሰሙትን ኣይነት ድምፅ አሰማ።

ጥዝጣዜ "ጠዘጠዘ" ስር ተመ.

ጥዩፍ "*ፀየፈ" ስር "ፅዩፍ"ን ተመ.

ጥያቄ "ጠየቀ" ስር ተመ.

ጥይት ስ ውስጡ በባሩድ የተሞላና አረር የተገጠመለት ቀለሀ (በጠመንጃ፣ በሽጉጥ ተደርጎ ከምሱሩ ሲወጋ ተቀጣጥሎ የሚፈነዳ ወይም የሚተኮስ)።



የጥይት ራት ሆነ በጥይት ተመትቶ ሞተ።

ጥይት ነው ጎበዝ፣ፈጣን፣ቀልጣፋ ነው።

ጥድ(ፅድ) ስ እንጨቱ ጠንካራ የሆነ ትልቅ የዛፍ ኣይነት።

ጥድፊያ "*ጠደፈ" ስር ተመ.

ጥዶ ዘለል "ጣደ" ስር ተመ.

ጥጃ ስ ከእምቦሳ ከፍ የሚልና ሳር መብላት፣ ውሃ መጠጣት የጀመረ የላም ልጅ።

ጥጃ ሆድ ቅ ሆዱ ቀዝር ያለ።

ጥጋት ስ ጥጃ ያላት፣ የምታጠባና የምትታለብ ላም።

ጥገና "ጠገነ" ስር ተመ

ጥገኛ "*ጠጋ" ስር ተመ.

ጥጉብ "ጠገበ" ስር ተመ.

ጥጋበኛ ዝ.ከ.

ጋብ ዝ.ከ.

ጥጋት^{1} ስ ያልታረሰ ወይም እጻሬ የሆነ መሬት።

ጥጋት^{2} ስ ጥግ።

ጥጋጥግ "*ጠጋ" ስር ተመ.

ጥግ ዝ.ከ

ጥግን "ጠገነ" ስር ተመ.

ጥጥ ስ 1. በቆላ አካባቢ የሚበቅል፣ እምቡጡ ሲፈነዳ በውስጡ ለልብስና ለሌላም አገልግሎት የሚውል ለስላሳ የሆነ ነጭ ቃጫ የሚገኝበት ተክል። 2. ከጥጥ ተክል የሚገኝ ተባዝቶና ተፈትሎ ድርናማግ የሚሆን ልስልስ ቃጫ፣ ፍንድ።

[የ] **ጥጥ ፍሬ (ጥፍጥሬ)** ስ በጥጥ ውስጥ የሚገኝ ጥቁር ፍሬ።

የጥጥ ፍንድ ስ ሊለቀም የደረሰና እምቡጡ የፈነዳ ጥጥ።

ጥጥር "ጠጠረ" ስር ተመ.

ጥፉ "ጠፋ^{1}" ስር ተመ.

ጥፊ "ጠፋ^{2}" ስር ተመ.

ጥፋተኛ "ጠፋ^{1}" ስር ተመ.

ጥፋት ዝ.ከ.

ጥፌ^{1} ስ ቅጠሉ ጫት የሚመስልና የእከክ ወይም የችፌ መድሃኒት ይሆናል የሚባል፣ ግንዱ ለእርፍና ለሞፈር ስራ የሚያገለግል የዛፍ አይነት።

ጥፌ^{2} "ጠፋ^{1}" ስር ተመ.

ጥፍሪንዶ "ጥፍርንዶ"ን ተመ

ጥፍር ስ በእጅና በእግር ጣት ጫፍ ላይ የሚበቅል ጠንካራ የሆነ የአካል ክፍል።

የጥፍር ሞረድ ስ ለጥፍር መሞረጃና ማለስለሻ የሚያገለግል አነስተኛና ሸካራ ብረት።

የጥፍር ቀለም ስ ሴቶች ጥፍራቸውን የሚያስውቡበት ቀለም።

ጥፍረ መጥምጥ ስ ጥፍር ላይ በሚደርስ አደጋ ምክንያት የሚመጣና ጥፍርን የሚያወልቅ ወይም የሚያጠቁር ህመም።

ጥፍራም ቅ (ስድብ) ባለጌ፣ ስድ።

ጥፍርንዶ(ጥፍሪንዶ) ስ ወተት የሚመስል ፈሳሽ ነገር የሚወጣው፣ ልጡ ለቁግ (ለጅራፍ ጫፍ) የሚሆንና እንደ ጥጥ ያሉ አበባዎች የሚያወጣ የእፅዋት አይነት።

ጥፍጥሬ "ጥጥ" ስር "ጥጥፍሬ"ን ተመ.

ጥፍጥፍ "ጠፈጠፈ" ስር ተመ.

ጦ የ "ጠ" ፊደል ሳብእ ዘር።

***ጦለ**

ተጦለ ግ ግርዱና ገለባው ከፍሬው (ከምርቱ) ተለየ።

አጦለ ግ በማጦያ ግርድን፣ ገለባን ከፍሬው ለየ።

ማጦያ ስ ከሰንደዶ ወይም ከጭራንፎ እንደ መጥረጊያ ሆኖ የሚሰራ ግርድንና ገለባን ከፍሬው ለመለየት የሚያገለግል እቃ።

***ጦለጦለ**

ጦልጧላ ቅ (ስድብ) ከውካዋ፣ ዘዋሪ።

ተንጦለጦለ ግ ተንከወከወ፣ እርፍ አልቀመጥ አለ፣ እዚያም እዚያም ሄደ።

አንጦለጦለ ግ እንከወከወ፣ አዞረ።

ጦሊት ስ ሴቶች በአንገታቸው ላይ የሚያደርጓትና በሁለቱም ጫፎች በኩል ጥለት ያላት አንድ አርብ ነጠላ።

ጦልጧላ "*ጦለጦለ" ስር ተመ.

ጦሎታ ስ ሲገርፉበት ወይም ሲያወናጭፉት ድምፅ የሚያሰማው ወይም የሚጮህው የጅራፍ ጫፍ፣ ቁግ።

ጦመ "ፆመ"ን ተመ.

ጦማር ስ ደብዳቤ፣ በፅሁፍ የሰፈረ መልእክት።

ጦረ (ጠወረ) ግ ያረጀን ወይም የደከመን ሰው ረዳ፣ አገዘ፣ ተንከባከበ (በምግብ፣ በልብስ፣ በመጠለያና በመሳሰሉት)።

ጡረታ ስ 1. የመንግስት ወይም የግል ድርጅት ሰራተኛ በአገልግሎት ላይ እያለ በደንቡ መሰረት የተወሰነ ገንዘብ በየወሩ በተቀማጭ መልክ ከደመወዙ እየተቀነሰ የሚቀመጥበትና አቅሙ ሲደክም ወይም የእድሜ ገደቡ ሲደርስ ከስራ ውጪ ሆኖ ለራሱ ወይም ለቤተሰቡ የመተዳደሪያ አበል የሚሰጥበት ሁኔታ። 2. ሽማግሌን ወይም አቅመ ደካማን በኑሮ የመርዳት ተግባር።

ጡረታ ወጣ የተወሰነው የእድሜው ገደብ በመድረሱ ወይም በህመም ምክንያት የነበረበትን የስራ ቦታ ለቀቀ፣ ከስራ ተሰናበተ።

የጡረታ አበል ስ በጡረታ ላይ ላለ ሰው የሚከፈል ገንዘብ።

ጡረተኛ ስ የእድሜው ገደብ በመድረሱ፥ ወይም በሌላ ምክንያት ስራ ያቆመ ወይም ከስራ የተሰናበተ ሰው።

ጥውር ቅ ኑሮው በቤተሰብ፥ በወዳጅ፥...የሚረዳ፥ ተጠዋሪ።

ጧሪ ቅ በሽምግልና ወይም በእርጅና ጊዜ የሚረዳ፥ የሚያግዝ፥ የሚንከባከብ።

ተጦረ(ተጠወረ) ግ በሽምግልና ወይም በእርጅና ጊዜው እየተረዳ ኖረ።

ተጧሪ(ተጠዋሪ) ቅ እየተረዳ የሚኖር።

ጦር ስ ከብረት የሚሰራና በሁለቱም ጎኑ ስለታም የሆነ ሹል ጫፍ ያለው ለመውጊያ የሚያገለግል መሳሪያ። 2. በጦርነት ጊዜ የሚሰለፍ ሰራዊት፥ወታደር፥...። *ጦር መጣ።*

እንደጦር ይፈራል ከመጠን በላይ ይፈራል። *ሰውዬውን እንደ ጦር ይፈሩታል።*

ጦሩ ተፈታ ተዋጊው ሰራዊት ተሸነፈ፥ ድል ሆነ።

ጦር ሰበቀ ለመወርወር ወይም ለመውጋት ጦሩን ነቀነቀ፥ ተዘጋጀ።

[የ] ጦር ሃይሎች ስ የምድር ጦርን፥ የአየር ሃይልን፥...የመሳሰሉ የተለያዩ የጦር ሰራዊት ክፍሎችን የሚያጠቃልል መጠሪያ።

የጦር ልምምድ ስ ብቃትን ከፍ ለማድረግ የሚካሄድ የውጊያ ልምምድ።

የጦር መሪ ስ በጦርነት ላይ የተሰለፈ ተዋጊ ቡድንን የሚመራ የበላይ አዛዥ፥ አዝማች።

የጦር መሳሪያ ስ የሞት ወይም የማቁሰል አደጋ ወይም ሌላ ጥፋት ሊያደርስ የሚችል እንደ ጦር፥ ሽጉጥ፥ ቦምብ፥... ያለ መሳሪያ።

የጦር መኮንን ስ ከምክትል መቶ አለቃ ጀምሮ ከፍተኛ ማእርግ ያለው የጦር ሰራዊት ባልደረባ።

የጦር ምርኮኛ ስ በጦርነት ጊዜ ተማርኮ የተያዘ ተዋጊ።

[የ] ጦር ሰራዊት ስ የአንድን ሃገር ዳር ድንበር የሚጠብቅና ሉአላዊነትን የሚያስከብር ወታደራዊ ሃይል።

የጦር አማካሪ ስ በጦር ሃይሎች ውስጥ ልዩ ልዩ ምክሮችና አስተያየቶችን የሚሰጥ የሰለጠነ ወይም ልምድ ያለው የጦር መኮንን።

የጦር አበጋዝ ስ የጦር መሪ።

የጦር አካዴሚ ስ ከፍ ያለ ወታደራዊ ሙያ የሚቀሰምበት የትምህርት ተቋም።

የጦር አዛዥ ስ የጦር ሃይል ክፍልን ለማንቀሳቀስ ወይም ለማዘመት የሚችልና ትእዛዝ የሚሰጥ ከፍተኛ ባለስልጣን።

የጦር አዝማች ስ የጦር መሪ።

የጦር ካሳ ስ በጦርነት ላይ ለደረሰ ጉዳት አጥፊው ወገን ለተጎጂው የሚከፍለው ካሳ።

የጦር ወንጀለኛ ስ በጦርነት ጊዜ እስረኞችን ያላግባብ የማሰቃየት፥ ሰላማዊ ሰዎችን የመጨፍጨፍና የመሳሰሉትን ኢሰብአዊ ድርጊቶች የፈፀመ ሰው።

የጦር ገበሬ ስ ሃይለኛ ተዋጊ።

የጦር ጉዳተኛ ስ በጦርነት ላይ የመቁሰል አደጋ የደረሰበት ወታደር ወይም ተዋጊ።

ጦር ሜዳ ስ ጦርነት የተደረገበት ወይም የሚካሄድበት ቦታ።

የጦር ሜዳ መነፅር ስ በጦርነት ጊዜ የሚገለገሉበት ሩቁን አቅርቦ የሚያሳይ መነፅር።

ጦር ሰፈር ስ ወታደር ወይም ሰራዊት የሰፈረበት ቦታ፥ ካምፕ።

ጦር ውርወራ ስ ከተወሰነው ቦታ ላይ በመሆን ጦርን እርቆ ለመወርወርና አሸናፊ ለመሆን የሚደረግ ስፖርታዊ ውድድር።

ጦር ግንባር ስ የውጊያ፥ የፍልሚያ ቦታ፥ የጦርነት መስመር።

ጦር ጠማሽ ቅ ጦርነት ናፋቂ ወይም ፈላጊ።

ጦረኛ ቅ 1. የጦርነት ዘዴ ወይም ስልት አዋቂ፥ የጦር ጀግና። 2. ጦር ጠማሽ። ✓

ጦርነት ስ 1. በተቃራኒ ወገን ወይም ሃገሮች መካከል የሚደረግ የመሳሪያ ውጊያ፥ ፍልሚያ። 2. ትግል፥ ግብግብ። *እቃ ለመግዛት ያለው ጦርነት ከባድ ነው።*

የጦርነት ደመና አንዣቧል ጦርነት ሊጀመር ወይም ሊካሄድ ተቃርቧል።

ጦርነት አወጀ ጦርነት እንደሚጀመር ወይም እንደሚካሄድ በይፋ ተናገረ።

ጦርነት ከፈተ ውጊያ ጀመረ።

ጦስ ስ 1. ሰበብ፥ ምክንያት። 2. ችግር፥ መዘዝ፥ መከራ።

ጦሰኛ ቅ መዘዘኛ።

ጦስኝ ስ በደጋና በወይና ደጋ የሚበቅል፥ ጥሩ ሽታ ያለውና ለቅመምነት የሚያገለግል አነስተኛ የእፅዋት አይነት።

ጦሽ

ጦሽ አለ ግ 1. እርጥብ እንጨት ሲነድ

የሚያሰማውን ዓይነት ድምፅ አሰማ። 2. ፈነዳ። 3. በሃይል ሳቀ ወይም አለቀሰ።

ጦሽ አደረገ ግ 1. አፈነዳ፥ አጮሀ። 2. በሃይል አሳቀ ወይም አስለቀሰ።

ተንጦሸጦሸ ግ ተንጣጣ።

አንጦሸጦሸ ግ አንጣጣ (በመቁላት፥ በመጥበስ፥ በመተኮስ፥..)።

***ጠነጠነ**

ጠንጧና ቅ ክውካዋ፥ ጠልጧላ፥ ዘዋሪ።

ጡንጡን አለ ግ ክውክው፥ ጡልጡል አለ።

አጠነጠነ ግ ወዲያ ወዲህ ተንከወከወ፤ ጡልጡል አለ።

ጦዘ ግ ከረረ፥ ተጠመዘዘ (ክር)። 2. (ዘይ.) ተጋጋለ፥ ሞቀ።

ጡዘት ስ በልብወለድ ፅሁፍ፥ በፊልም፥... ውስጥ የታሪኩ ሂደት ከፍተኛ ቦታ የሚደርስበትና ስሜት የሚይዝበት፥ በስተመጨረሻ አካባቢ ያለው የድርሰቱ አካል።

አጦዘ ግ 1.አከረረ፥ጠመዘዘ።2. በሃይል መታ፥ ጠለዘ፥ ለጋ (ኳስን)። 3.(ዘይ.) መታ፥ ደበደበ።

ጦዘጦዘ ግ አረጀ፥ ሸመገለ።

ጦዝጧዛ ቅ ያረጀ፥ የሸመገለ።

***ጠዘጠዘ**

ጦዝጧዛ ቅ ክውካዋ።

ተንጠዘጠዘ ግ ተንከወከወ።

አንጠዘጠዘ ግ አንከወከወ።

ጦዝጧዛ^{1} "ጦዘጦዘ" ስር ተመ.

ጦዝጧዛ^{2} "*ጠዘጠዘ" ስር ተመ.

ጦጣ ስ እንደ ዝንጀሮና ጉሬዛ ከዛፍ ላይ የሚወጣ፥ ብልጥ ነው የሚባል የዱር እንሰሳ።(ስእሉን የዱር እንስሳት ስር ተመ.)

ጦፈ ግ 1. ነደደ፥ ተቃጠለ፥ ተንቀለቀለ (እሳት)። 2. (ዘይ.) በሃይል ተበሳጨ፥ ተናደደ። 3. ደመቀ፥ ተሟሟቀ። *ጨዋታው ጦፈ።*

ጧፍ ስ ለመብራት የሚያገለግል በሰም የተነከረ ክር ወይም ፈትል።

ተጧጧፈ ግ 1. ተቀጣጠለ፥ ተያያዘ (እሳት)። 2.ሞቀ፥ ደራ፥ ተጋጋለ።(ለምሳሌ ወሬ፥ ጦርነት፥...)።

አጧጧፈ ግ በሰፊው አካሄደ።*ንግዱን አጧጡፎታል።*

ጧ^{1} የ "ጠ" ፊደል ፍንፅቅ ዘር።

ጧ^{2}

ጧ ብሎ ተኝቷል ሃይለኛ እንቅልፍ ወስዶታል።

ጧ አለ ግ 1. አንድ ነገር ሲበጠስ ወይም ሲፈነዳ የሚያሰማውን ዓይነት ድምፅ አሰማ። 2. ተበጠሰ። 3. ፈነዳ። 4.ጓ አለ፥ ተዘረረ፥ ተዘረጋ።

ጧ ያለ ሜዳ ስ ወጣ ገባ የሌለው ሰጥ ያለ ሜዳ።

ተንጧጧ ግ ተንጣጣ፥ ተንጦሸጦሸ፤ ደጋግሞ ፈነዳ።

አንጧጧ ግ አንጣጣ፥ አንጦሸጦሸ፤ አፈነዳ።

ጧሪ "ጦረ" ስር ተመ.

ጧት (ጠዋት፥ ጥዋት) ስ ማለዳ፥ ንጋት ላይ ያለው ጊዜ።

ጧፍ "ጦፈ" ስር ተመ.

ጨ

ጨ ከ "ጠ" ፊደል ዘር ቀጥሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል (ግእዙ ሆሄ)።

ጨለሀ ግ ደረቀ፣ ከረረ።

ጨለሄ ቅ ድርቅ ያለ፣ የከረረ።

ጨለመ ግ 1. ማታ ሆነ፥ የፀሃይ ብርሃን አለፈ፥ መሸ። 2. አልታይ አለ፣ ብርሃን ታጣ። *ቤቱ ጨለመ*። 3. ከለለ፣ ጋረደ፣ ሸፈነ። *ትርኢቱን እንዳላይ ጨለምከኝ*። 4. ጠቆረ።

ጨለመበት የሚያደርገው ግራ ገባው።

ጨለማ(ጭለማ) ስ የፀሃይም ሆነ የሌላ ነገር ብርሃን የሌለበትና ማየት የማይቻልበት ቦታ ወይም ጊዜ።

ጨለማ ለበሰ 1. ጠቆረ። 2. ጨለማን ተገን አደረገ፥ ተከለለ።

ጨለማ በሳኝ ረዳት ወይም ደጋፊ አጣሁ፥ ለችግር ተጋለጥኩ።

ጨለማ ዋጠው 1. ጥቅጥቅ ባለ ጨለማ ውስጥ ሆነ። 2. ግራ ገባው፥ ጨነቀው፥ የሚያደርገውን አጣ።

ጨለማን ተገን አደረገ ጨለማን ተከለለ(ተደብቆ ጉዳት ለማድረስ፥..)።

ጨለማው ገፈፈ ጨለማው ተወገደ፥ብርሃን ሆነ።

ጨለማ ፊት 1. ጥቁር የሆነ(ሰው)። 2. ፊቱ ላይ ፈገግታ ወይም ደስታ የማይታይበት፣ ያዘነ፥ የተቆጣ፥ የተቸገረ፥ ሁሌ የከፋው የሚመስል።

አጨለመ ግ 1. ብርሃን አሳጣ። 2. አሰናከለ፥ አበላሸ (እድልን፥ ተስፋን፥...)።

*ጨለቀ

ጭለቃ ስ ከማር ወይም ከስኳር ጋር የተመታ የተልባ ወይም የኑግ ወይም የሰሊጥ ብጥብጥ።

አጨለቀ ግ ኑግን ወይም ተልባን ወይም ሰሊጥን ከማር ወይም ከስኳር ጋር አሸ፥ መታ፥ በጠበጠ።

ጨሊቁ ስ በአብዛኛው ሙሉ በሙሉ ቢጫ ሆኖ ከክንፎቹ በላይ አሸዋማ የሆነ መልክ ያለውና የተዘራ እህል የሚበላ ወማይ የሚያክል ወፍ (ስእሉን ወፍ ስር ተመ.)።

ጨለቅለቃ ስ አይን ላይ የሚያንፀባርቅ ወይም የሚያብረቀርቅ በሰፊው የተንጣለለ ውሃ።

ጨለጠ ግ 1. ባዶ አደረገ፥ ጨረሰ፥ አጠነፈፈ (ፈሳሽን፥ መጠጥን)። 2. ጨርሶ ጠጣ።

ጨላጣ ቅ (ስድብ) የማይጨበጥ፥ ሞላጫ፥ ቀሸ።

ጭላጭ ስ በብርጭቆ ወይም በሌላ እቃ ውስጥ በትንሹ የቀረ ፈሳሽ።

ጭልጥ አለ ግ 1. በሄደበት ቀረ፥ ቆየ፥ ጠፋ። 2. ሄደ፥ ነጎደ፥ እብስ አለ(በሃሳብ፥ በአካል)። 3. አለቀ፥ ተሟጠጠ (ለፈሳሽ ነገር)።

ጭልጥ ያለ እልም ያለ፥ በሃይል፥ በጣም___ የሆነ። *ጭልጥ ያለ ሌባ /ጭልጥ ያለ ውሸታም*።

ጭልጥ ያለ ገደል ጅው ያለ ረጅም ገደል።

አጫለጠ ግ 1. ከዚያም ከዚህ እያንቃረረ ቀዳ ወይም ጠጣ። 2. አብሮ ጠጣ፥ አጣጣ (የመጠጥ ጓደኛ)።

አጫላጭ ስ የመጠጥ ቤት ጓደኛ።

አንጫለጠ ግ ጠጣ።

ጨለጨለ ግ ለመለመ፥ አቆጠቆጠ(የበልግ እህል፥ ሳር)።

ጨሌ ስ አዲስ የወጣ ለምለም ሳር ወይም ቡቃያ።

ጭል ጭል አለ ግ 1. መብቀል ጀመረ(ሳር)። 2. በትንሽ በትንሹ ወረደ፥ ፈሰሰ (ፈሳሽ)። 3. በትንሽ በትንሹ ታየ፥ ሆነ፥ ተደረገ።

አጨለጨለ ግ አቆጠቆጠ፥ አበቀለ፥ መለምለም ጀመረ።

ጨለፈ ግ 1. በጭልፋ፥ በጣሳ፥... አወጣ፥ ቀዳ፥ ጠለቀ (ወጥን፣ ፈሳሽን፣..)።2. በጥቂቱ ወሰደ፥ ቀነጠሰ (ነገርን፥ ትምህርትን፥ ...)። 3. ነጠቀ፥ ቀማ።

መጨለፊያ(መጭለፊያ) ስ ጭልፋ።

ጭሉፋት(ጩሉፋት) ስ ቀማኛ፥ ነጣቂ፥ሌባ።

ጭልፋ ስ ወጥን፥ ፈሳሽ ነገርን፥ ንፍሮን፥... ከጎድጓዳ እቃ ውስጥ (ድስት፥ሳህን፥ ማሰሮ) ለማውጣት እንዲያገለግል ከእንጨት ወይም ከብረት ወይም ከቀንድ፥... የተሰራ ጎድጎድ ያለ ባለ እጀታ እቃ።

ጨላጣ "**ጨለጠ**" ስር ተመ.

ጨሌ "**ጨለጨለ**" ስር ተመ.

ጨሌ ስ ጥቃቅንና ክብ ሆኖ ከመስታወት ማእድን በተለያዩ ቀለማት የተሰራ፥ በክር ተሰክቶ የሚያያዝበት ቀዳዳ ያለውና ለአምልኮት፥ ለጌጥ፥...የሚጠቀሙበት ዶቃ መሰል ጌጥ።

ጨሌ ጣለ በጨሌ ጠነቆለ።

ጨሌ ጣይ ስ በጨሌ የሚጠነቁል።

ጨሌያም ቅ (ስድብ) በጨሌ፥ በጥንቆላ የሚያምን።

ጨሌ ባለጋሜ ስ እንደ ደጋን ቆልመም ያሉ ቀንዶችና ረዥም ሆነው ጫፋቸው ላይ ፀጉር ያሉባቸው ጆሮዎች ያሉት፥ ብዙውን ጊዜ ሳር፥

ቅጠላቅጠልና ውሃ በሚገኝበት ቆላማ ስፍራ የሚኖርና እንደ ፈረስ ጋማ ያለው ትልቅ የዱር እንስሳ ፤ ቶራ ፈረስ።

***ጨመለቀ**

ጨምላቃ (ጨመለቅ) ቅ 1. (ስድብ) እድፋም፥ ቆሻሻ። 2. (ስድብ) ለፍዳዳ፡ ሞልቃቃ፥ ባለጌ።

ጭምልቅ አለ ግ 1. በቆሻሻ ተበከለ፥ ተልከሰከሰ። 2. ጨቀየ፡ ዳጥ ወይም ጭቃ ሆነ። 3. ተሞላቀቀ፥ ተስፋደደ።

ጭምልቅ አደረገ ግ 1. ለወሰ፥ አጨማለቀ (በጭቃ፥ በቆሻሻ)። 2.አሞላቀቀ፡ አባለገ(ልጅን)።

ተጨማለቀ ግ 1. በጭቃ ወይም በቆሻሻ ተለወሰ፡ ተነካካ፥ ተበከለ። 2. ተንከረ፥ ተዘፈቀ። *በእዳ ተጨማልቋል*። 3. ተሞላቀቀ፥ ተስፋደደ፡ ባለገ።

አጨማለቀ ግ 1. አባለገ፥ አሞላቀቀ(ልጅን)። 2. በጭቃ ወይም በቆሻሻ፥... ለወሰ፥ አነካካ።

ጨመረ ግ 1. አከለ፥ በነበረው ላይ ደመረ። 2. አበረከተ፥ አበዛ። 3. አገባ፥ ዶለ፥ ከተተ። 4. አደገ፥ ትልቅ ሆነ። 5. በዛ፡ በረከተ። 6. ከፍ አደረገ። *ፍጥነቱን ጨመረ*።

ጭማሪ ቅ ፊት በነበረው ላይ በኋላ የታከለ፥ የተጨመረ (ደሞዝ፥ ገንዘብ ወይም ሌላ ነገር)።

ጭምር መዋ. በተጨማሪ፥ አንድ ላይ፥ አብሮ። *አንተም ጭምር እንድትመጣ*።

ተጨመረ ግ 1. ቀድሞ በነበረው ላይ ተደመረ፥ ታከለ። 2. ከፍ አለ። *ደሞዝ ተጨምሮለታል*። 3.አንድ ሆነ፥ አበረ።*ልጁም ከአባቱ ጋር ተጨምሮ ሰደበኝ*።

ተጨማሪ ቅ 1. በነበረው ላይ የታከለ፥ ተደራቢ። ስ 2. በፊት የተነገረውን የሚያጎለብት፥ የሚያበረታ ተመሳሳይ ወይም ተቀራራቢ ሃሳብ፥ አስተያየት።

በተጨማሪ በተደራቢ፥ ሌላ፡ በማከልም ለማለት የሚያገለግል ቃል። *በተጨማሪ በቅርብ ቀን እንደምመጣ ለገለፅልህ እወዳለሁ*።

ተጨማመረ ግ ታከለ፥ ተደመረ።*ሌሎች ወጪዎች ሲጨማመሩ ገንዘቡ ይበዛል*።

ጨመቀ ግ 1. ፍራፍሬን ወይም ሌላ ነገርን በእጅ ወይም በመሳሪያ በመጫን ፈሳሹን ከውስጡ አወጣ። 2. እርጥብ ልብስንና የመሳሰለውን ነገር በሃይል በመጫን፡ በመጨበጥ፥ በመጠምዘዝ ያዘለውን ውሃ አስወገደ፥ አንጠፈጠፈ። 3. እንባ እንዲወጣው አይኑን ጭፍን ጭፍን አደረገ። 4. (የፅሁፍን፡ የንግግርን) ሃሳብ አሳጠረ፥ ፍሬ ነገሩን አጣርቶ አወጣ።5. በጣም፥ በሃይል ተጫነ ወይም አጠበቀ (ሲያቅፍ ሲጨብጥ።)

መጭመቂያ ስ እንደብርቱካን፥ አናናስ፥ ማንጎ፥... ያሉት ፍራፍሬዎች የሚጨመቁበት ወይም ከተለያዩ እፅዋት ዘይትን ወይም ሌላ ነገርን ጨምቆ ለማውጣት የሚያስችል መሳሪያ።

ጭማቂ ስ 1. ከብርቱካን፥ ከአናናስ፥ ከማንጎ፥... ተጨምቆ የወጣ መጠጥ። 2. ባጭሩ ተውጣጥቶ የቀረበ የሃሳብ ወይም የፅሁፍ ፍሬ ነገር።

ጨመተ ግ 1. አረመመ፥ ዝምተኛ ሆነ። 2. ረጋ፥ አደብ ገዛ፥ መንቀዥቀዥ ወይም መከለፍለፍ ተወ።

ጭምት ቅ 1. ዝምተኛ። 2. ረጋ ያለ፥ አደብ ያለው፡ የማይንቀዠቀዥ።

አጨመተ ግ ጭምት አደረገ።

ጨመተረ ግ የሰውነት ቆዳን ወይም ሌላ ነገርን አኮማትሮ ወይም አጨማድዶ ያዘ፥ ሸበሸበ፡ ጨረመተ (እርጅና፥ እሳት፥...)።

ጨምታራ ቅ ኮምታራ፥ ጨምዳዳ፥ ጨርማታ።

ተጨማተረ ግ ተኮማተረ፥ ተጨማደደ፥ ተጨረመተ።

አጨማተረ ግ አኮማተረ፥ አጨማደደ፥ አጨረመተ።

ጨመደደ ግ 1. ሸበሸበ፥ ሸመቀቀ፡ጨመተረ። 2. አጥብቆ ያዘ፥ ጨበደ፡ እንቅ አደረገ። 3. እንዳይንቀሳቀስ አለ፥ ጨበጠ፥ ቀሰፈ (ህመም)።

ጨምዳዳ ቅ 1. የተጨማደደ፥ የተሸበሸበ። 2. (ስድብ) ፊቱ የማይፈታ፥ ሁሌ የተከፋ የሚመስል። 3.ጨባጣ፥ ጨርማታ።

ተጨማደደ ግ ተጨማተረ፥ ተኮማተረ፥ ተሸማቀቀ።

አጨማደደ ግ አጨማተረ አኮማተረ፥ አሸማቀቀ።

ጨመገገ ግ ጨፈገገ፥ ቅጥርጥርአደረገ፥ አጠቆረ(ለምሳሌ ፊትን በብስጭት፡ በመከፋት፥..)።

ጨመጨመ^{1} ግ ደጋግሞ ወይም መላልሶ ሳመ።

ጨመጨመ^{2} ግ በቤት ዋልታ ዙሪያ ማገር አሰረ፥ ታታ፥ ጠመጠመ።

ጭምጭማት ስ በዋልታ ዙሪያ ተጠጋግተው የሚማገሩ ወይም የሚታቱ ቀጫጭን ማገሮች በአንድነት።

ተጨመጨመ ግ በቤት ዋልታ ዙሪያ ማገር ተሰራ፥ ተታታ፥ ተጠመጠመ።

ጨምላቃ "***ጨመለቀ**" ስር ተመ.

ጨምባሳ "**ጨነበሰ**" ስር ተመ.

ጨምታራ "**ጨመተረ**" ስር ተመ.

ጨምዳዳ "**ጨመደደ**" ስር ተመ.

ጨምጫማ ቅ አይኑ ጭፍንፍን ያለና እንባ ያዘለ። *አይኑ ጨምጫማ*።

*ጨረመመ

ጨርማማ ቅ 1. የተወላገደ፣ የተጨራመተ፣ ስርጉድጉድ። 2. (ስድብ) ጨርማታ፣ ፊቱ የተጨማደደ።

ተጨራመመ ግ ተጣመመ፣ ተጨራመተ፣ ተወላገደ።

አጨራመመ ግ አጣመመ፣ አጨራመተ፣ አወላገደ።

*ጨረመተ

ጨርማታ ቅ 1. ጉብጥብጥ ያለ፡ የተሰረጎደ፣ የተወላገደ(ቆርቆሮ ወይም ሌላ ነገር)። 2. (ስድብ) ሰውነቱ የተጨማደደ፣ያረጀ ወይም በጣም የሸመገለ።

ተጨራመተ ግ ጉብጥብጥ፣ እጥፍጥፍ አለ፣ ተከማተረ።

አጨራመተ ግ ጉብጥብጥ፣ እጥፍጥፍ፣ ውልግድግድ አደረገ፤ ሰረጎደ፤ አከማተረ።

*ጨረረ[1]

ጭርር አለ ግ እርር፣ ድብን፤ ቅጥል አለ።

ጭርር አደረገ ግ እርር፣ ድብን፤ ቅጥል አደረገ።

ተንጨረረ ግ 1.ተቃጠለ፣ አረረ፣ ደበነ፣ ተከማተረ(በፀሃይ...) ። 2.ደበነ፣ አረረ (በንዴት)።

አንጨረረ ግ አቃጠለ፣ አሳረረ፣ አደበነ፣አከማተረ።

*ጨረረ[2]

ጨረራ ስ 1. ጨረር። 2. ከኤሌክትሪክ ወይም ከሌላ ተመሳሳይ ነገር የሚመነጭ የብርሃን ሃይል ወይም ሙቀት።

ጨረር ስ 1. ከፀሃይ የሚፈነጠቅ ብርሃን፣ ጮራ።2. በጣሪያ፡ በግድግዳ፡ በበር፡ በመስኮት ብስ በኩል ወይም ቀዳዳ የሚገባ የፀሃይ ብርሃን።

የጨረር ሃይል ስ ከፀሃይ ብርሃን ወይም ሙቀት የሚገኝ ሃይል ወይም ጉልበት።

ጮራ ስ ከፍተኛ ሃይል የሌለውና ፀሃይ ስትወጣ ፍንጥቅጥቅ ብሎ የሚታይ የፀሃይ ብርሃን፤ የብርሃን ፍንጣቂ።

ጨረሰ ግ 1. አጠናቀቀ፡ ፈፀመ፡ ከወነ፣ ደመደመ፡ አበቃ፡ አከተመ። 2. ባዶ አደረገ፡ አሟጠጠ። *ምግቡን ጨረሰ።* 3. ገደለ።4. ጉዳት አደረሰ። *ተባይ ጨረሰን/ ሌባ ጨረሰን።* 5. የተወሰነ ጊዜ (ቀን ወር፡...) ወሰደ፣ ፈጀ። *ስራው አስር ሳምንት ጨረሰ።* 6. ፈጀ፣ ተጠቀመ። *በዚህ ወር ብዙ ማገዶ ጨርሰናል።* 7. በላ። *መኪናዋ ለ5 ኪሎ ሜትር ጉዞ ሁለት ሊትር ቤንዚን ትጨርሳለች።* 8. ካለበት ደረጃ በላይ መሄድ የማይችልበት ሁኔታ ላይ ደረሰ፣ አሟጠጠ። *ትእግስቱን ጨረሰ።* 9. አለቀበት። *ልብሱን ጨርሷል።*

ጨርሶ ተው.ግ. ፈፅሞ። *አረቄን ጨርሶ አይጠጣም/ ጨርሶ ይገርሀ።*

መጨረሻ ተው.ግ 1.መፈፀሚያ ፣ ማብቂያ፣ ማጠናቀቂያ። 2 በቃ፣ ከሁሉም በስተኋላ። *መጨረሻ ላይ መጣች ከሁሉም የተሻለ ውጤት አገኘ።*

በመጨረሻ በማጠቃለያ ወይም በጠቃላይ ለማለት የሚያገለግል የአረፍተ ነገር ማያያዣ። *በመጨረሻ ለገለፃ የምፈልገው...።*

በመጨረሻው ሰአት ለፍፃሜ ትንሽ ሲቀረው ወይም የተወሰነው ጊዜ ሊያልቅ ሲል።*በመጨረሻዋ ደቂቃ የአሸናፊ ቃሉን ሰጠ/ በመጨረሻው ሰአት በምርጫው እንደሚሳተፍ ገለፀ።*

የመጨረሻ 1. የማይቀየር፣ የማይሻሻል፣ የማይለወጥ። *የመጨረሻ ቃል/ የመጨረሻ ትእዛዝ።* 2. እቻ የማይገኝለት። *የመጨረሻ ጥሩ ሰው ነው።* 3. ማሟጠጫ።*የመጨረሻ ልጆቸው ገብሬ ነው።*

ጭራሽ ተው.ግ. 1. በፍፁም፣ ፈፅሞ።*ጭራሽ አላገኘሁም።* 2. ይባስ ብሎ፣ እንዲያውም። *ይቅርታ እንደመጠየቅ ጭራሽ ታኮርፋለህ ?*

በጭራሽ ተው.ግ. በምንም አይነት፣ ፈፅሞ። *በጭራሽ ላልነግርህም።*

ጭራሹን ጭራሽ።

ጭርስ አለ ግ 1. ለሞት ተዳረሰ፣ ደከመ። 2. አለቀ።

ጭርስ አደረገ ግ 1.ፈፅሞ ጨረሰ፣ ምንም ሳይቀር አሟጠጠ። 2.አደከመ፣ ለሞት አደረሰ። *ሰውነቱን በሽታ ጭርስ አደረገው።*

ተጨረሰ ግ አለቀ። *ስራው መቼ እንደተጨረሰ አላውቅም።*

ተጫረሰ ግ ተፋጀ፣ ተጋደለ፣ ተላለቀ።

አጨራረስ ስ በአንድ የድርጊት ሂደት ማጠቃለያ ወይም ውጤት በማሳያ ደረጃ ላይ የሚታይ ክንዋኔ።*ቡድኑ ጥሩ ጫወታ ያሳይና አጨራረስ ላይ ደካማ ይሆናል።*

አጫረሰ ግ 1. የሌላውን ገንዘብ አብሮ በመጠቀም ቶሎ እንዲያልቅ አደረገ። 2. እርስ በርሱ እንዲገዳደል፣ እንዲተላለቅ አደረገ።

አጫራሽ ቅ የሌላውን ገንዘብ አብሮ በመጠቀም፣ ጤናን፣...እንዲባክን የሚያደርግ።

አስጨረሰ ግ 1. አስፈጀ፣ አስገደለ። 2. የተጀመረው ነገር፣ ወሬ፣ ስራ፣... እንዲያልቅ አደረገ።

*ጨረቀ

ጭርቂያም ቅ (ስድብ) ሽንታም።

ጭርቅ አለ ግ በትንሹ ፈሰስ ብሎ ቆመ

(ብዙውን ጊዜ ለሽንት)።

ጭርቅ አደረገ ግ በትንሹ ሸና፣ ጠብጠብ አደረገ።

አጨረቀ ግ ሽንቱን በትንሹ ሸና።

ጨረቂት ስ ንጣት ያለው የማሽላ አይነት።

ጨረቃ ስ በመሬት ዙሪያ እየዞረች ከፀሃይ የምታገኘውን ብርሃን ወደ መሬት የምትፈነጥቅ፣ ጠፈር ውስጥ ካሉት አካላት አንዷ ወይም በሌላ ፕላኔት ዙሪያ የሚዞር ተመሳሳይ አካል።

ጨረቃ ምድር ያዘች ኡደቷን ወደ መጨረስ ተቃረበች፣ ጧት ጧት መታየት ጀመረች።

ጨረቃ ተወለደች ጨረቃ በትንሹ ታየች፣ ተገለጠች፣ ብቅ አለች (እንደገና ኡደቷን ለመጀመር)።

ጨረቃ ነው የጨረቃ ብርሃን አለ (ማታ ወይም ሌሊት ላይ)።

ጨረቃ ወጣች ጨረቃ ብርሃኗን ሰጠች፣ አሳየች።

ጨረቃ የመሰለ ነጭ የሆነ፣ ፈካ ብሎ የሚታይ ።

የጨረቃ አር ስ ከእንጨት ላይ ተጣብቆ የሚገኝና ጠበቅ አድርገው ሲይዙት እርጥቡ የሚፈርጥ፣ ደረቅ ፍርክስ የሚል፣ ነጣ ወይም ቀላ ያለ እንጉዳይ መሰል ነገር።

ጨረቋ ግ ፍሬ ጀመረ፣ ጮርቃ ሆነ።

ጮርቃ ቅ 1. እንጭጭ፣ ለጋ (ፍሬ)። 2. በጣም ያላደገ፣ ያልጠና (ልጅ)። 3. (ዘይ.) በአስተሳሰቡ ያልበሰለ (ሰው)።

ጮርቃ በርበሬ ስ ያልበሰለ፣ ያልቀላ ቃሪያ በርበሬ።

ጨረባ ስ መልኩ ቡላ የሆነ የወፍ አይነት፣ በቋል፣ ጥሬ ፈጅ።

የጨረባ ተዝካር ጫጫታ የበዛበት፣ መደማመጥ የሌለበት፣ ስነ ስርአት ያጣ ስብሰባ ወይም ንግግር።

ጨረተ ግ በመንተብ፣ በመፋቅ፣ በመፋተግ ፀጉር ወይም ጭራ መሰል ነገር አወጣ።

ጭረት ስ በመንተብ፣ በማለቅ፣ በመፋተግ ምክንያት የወጣ ፀጉር ወይም ጭራ መሰል ነገር።

አጨረተ ግ ፋቀ፣ ፈገፈገ፣ ጭረት እንዲወጣ አደረገ።

***ጨረተ**

ጨረታ(ጫረታ) ስ አንድን ነገር የመሸጫ መነሻ ዋጋውን ወስኖ፣ ከዚያ በላይ ብልጫ ያለውን ዋጋ ለሚሰጥ ገዢ ለመሸጥ የሚዘጋጅ የዋጋ ውድድር(ፉክክር) ልዩ የሽያጭ ስርአት፡

ለጨረታ ቀረበ አንድ ነገር በጨረታ ወይም በውድድር ዋጋ አብለጠ ለከፈለ እንዲሸጥ ለገዢያ ወይም ለሽያጭ ቀረበ።

በጨረታ ገዛ አንድን ነገር በውድድር የተሻለ ክፍያ ሰጥቶ ገዛ።

ጨረታ ወጣ አንድ ነገር በጨረታ እንዲሸጥ ለገበያ ቀረበ።

ጨረታ አወጣ አንድን ነገር በጨረታ ለመግዛት ወይም ለመሸጥ ወይም አንድን ስራ ለማሰራት ለውድድር አቀረበ።

የጨረታ ማስታወቂያ ስ አንድን ነገር በጨረታ ለመግዛት፣ ለመሸጥ ወይም አንድን ስራ ለማሰራት ተጫራቾችን ለውድድር የሚጋብዝ ማስታወቂያ።

ተጫረተ ግ ለግዥ ወይም ለሽያጭ ወይም አንድን ተግባር ለማከናወን በዋጋ ተፎካከረ፣ ተወዳደረ (በፅሁፍ ወይም በቃል፣ በግልፅ ወይም በምስጢር)።

ተጫራች ቅ የጨረታ ተፎካካሪ፣ ተወዳዳሪ (ሰው)።

አጫረተ ግ በዋጋ አወዳደረ፣ አፎካከረ፣ አበላለጠ (በቃል ወይም በፅሁፍ፣ በግልፅ ወይም በምስጢር)።

አጫራች ቅ ጨረታ የሚያካሂድ (ሰው)።

ጨረነቀ ግ ጨቀነ፣ ተጫነ።

ጨርናቃ ቅ አንገተ አጭር (ሰው)።

ጨረገደ ግ 1. ሳርን፣ ቅጠልን፣... በአንድነት አጨደ። 2. መታ፣ ደበደበ (በሸመል፣ በዱላ፣...)። 3. በብዛት ጥርግ አድርጎ በላ።

***ጨረገገ**

ተንጨረገገ ግ ተንዠረገገ፣ ተንጠለጠለ(ፍሬ)።

እንጨረገገ ግ እንዠረገገ፣ ብዙ ፍሬ አፈራ።

***ጨረጨረ**

ጭርጭር አለ ግ ተንጨረጨረ።

ተንጨረጨረ ግ 1. ተጠበሰ፣ ተቆላ፣ በእሳት በጣም ተቃጠለ (ስጋ፣ ቅቤ፣...) ። 2. ተከነ፣ አረረ፣ ደበነ(በንዴት)።

እንጨረጨረ ግ 1. ጠበሰ፣ ቆላ፣ እስኪያር አቃጠለ። 2. አተከነ፣ አሳረረ፣ አናደደ፣ ክፉኛ አበሳጨ። 3. አስጮሀ።

ጨረጨሰ ግ በጣም አረጀ፣ ሸመገለ።

ጨርጫሳ (ጨረጨሰ) ቅ (ስድብ) ያረጀ ያፈጀ፣ አርጌ፣ ሸማግሌ ወይም አሮጊት።

ጨረፈ ግ በጨረፍታ መታ፣ ለኮፍ ወይም ነካ አደረገ።

ጨረፍታ ስ በመጠኑ፣ በከፊል፣ በትንሹ የማየት፣ የመስማት፣ የመምታት፣... ሁኔታ። *በጨረፍታ ላያት።*

***ጨረፈፈ**

ጭርፍፍ አለ ግ ተንጨረፈፈ።

ተንጨረፈፈ ግ ተንጨፈረረ፤ ተንዘረፈፈ።

አንጨረፈፈ ግ አንጨፈረረ፥ አንዘረፈፈ።

ጨረፍታ "ጨረፈ" ስር ተመ.

ጨርማማ "ጨረመመ" ስር ተመ.

ጨርማታ "ጨረመተ" ስር ተመ.

ጨርቅ ስ ከሱፍ ወይም ከጥጥ ወይም ከሃር ክር የሚዘጋጅና ለልብስ፣ ለመሸፈኛ፥ ለመጋረጃ+... የሚያገለግል የፋብሪካ ስራ ወይም የሽመና ውጤት።

ጨርቁን ጣለ አበደ፤ ወፈፈ።

ጨርቁን ማቁን አለ ሰበብ፥ ምክንያት አበዛ።

ጨርቅ ሆነ 1. ለሰለሰ፤ ለፋ (ቆዳ)። 2. በጣም ሰከረ። 3. በህመም ምክንያት ሰውነቱ መነመነ፥ ደከመ።

ጨርቅ ለባሽ (የን.አነ.) መናጢ ድሃ፡ ምንም የሌለው።

ጨርቃም ቅ (የን. አነ.) ቅርንጫሳም፥ ዘባተሏም፥ ቡትቷም።

ጨርናቃ "ጨረነቀ" ስር ተመ.

ጨርጫሳ "ጨረጨሰ" ስር ተመ.

ጨሰ (ጤሰ) ግ 1. በመንደድ፥ በመቃጠል ምክንያት በነነ፣ ተነነ፥ ተትጎለጎለ፡ ወጣ (ጢሱ፥ እንፋሎቱ)። 2. ተናደደ፤ ተበሳጨ። 3. በጣም ተወደደ፥ ዋጋ ቀጠለ።*የመኪና ዋጋ እንደድሮው አይደለም፤ ጨሷል።* 4. በጣም አረጀ፥ ጨረጨሰ። *የጨሰ ሽማግሌ።*

ሳይጨስ ነደድ ሲነድ ጪስ የማይወጣው ጭራሮ እንጨት።

ጪስ(ጢስ) ስ ማገዶ፥ ማእጠንት ወይም ሌላ ነገር ሲቃጠል ወይም በእሳት ሲያያዝ የሚፈጠረው ጉም ወይም እንፋሎት መሰል ነገር።

በጪስ በእያንዳንዱ ቤት።*በጪስ ሁለት ሁለት ብር ከፈልን።*

ጪስ መታው ጪስ ጨሰበት ወይም ጪስ መሰለ።

[የ] ጪስ እንጨት ስ ሲቃጠል ጪሱ ጥሩ ሽታ ያለው እንጨት።

ጪስ መውጫ ስ የመኪናን ወይም የሌላ ሞተርን ለማንቀሳቀስ የሚቃጠለው የቤንዚን ወይም የናፍታ ጪስ ወደ ውጭ የሚወጣበት ቧንቧ መሰል አሸንዳ።

ጪሰኛ (ጢሰኛ) ስ በሰው መሬት ላይ ቤት ሰርቶ እያረሰ ሲኖር፥ እርቦ ወይም እኩሌታ ለባለመሬቱ ይሰፍር የነበረ ገበሬ።

ተጫጫሰ ግ 1. ተያያዘ+ ተቀጣጠለ (እሳቱ)።2.ተጧጧቀ+ተጋጋለ (ጠቡ፥ ነገሩ+...)።

አጨሰ ግ 1. ማገዶን፥ የጢስ እንጨትን+ ማእጠንትን በማቃጠል ጪስ እንዲወጣ አደረገ። 2. ማገ+ ጠጣ(ትንባሆን፣ ሲጋራን)። 3. መታ (በጥፊ+ በጥይት)። 4. በጥሩ ዋጋ ሸጠ። 5. አበገነ+አናደደ።

ማጨሻ ስ እጣንና የመሳሰለው የሚጨስበት ገል ወይም ሌላ እቃ።

አጫሽ ስ ሲጋራ የሚያጨስ ወይም የሲጋራ ሱሰኛ።

አጫጨሰ ግ 1. አያያዘ+ አቀጣጠለ(እሳትን)። 2. አጧጧቀ፥ አጋጋለ (ጠብን፣ ነገርን)።

ማጫጫሻ ስ ማያያዣ ወይም ማቀጣጠያ ኩበት+ ፋንድያ+ ግብስብስ፣...።

ጨቀየ ግ በውሃ ወይም በዝናብ ራሰ+ በሰ+ ተጨማለቀ፥ ጭቃ ሆነ(መሬት)።

ጭቃ ስ 1.በዝናብ ወይም በውሃ የራሰ+ የበሰ ወይም የተጨማለቀ መሬት ወይም አፈር። 2. ማጥ+ አረንቋ፤ ረግረግ መሬት። 3. (ስድብ) ረሀጥ+ ሰነፍ (ሰው)።

ጭቃ መራጊ ስ ሙያው ግድግዳን በጭቃ መምረግ የሆነ ሰው። ጭቃ ረጋጭም ይባላል።

ጭቃ ረገጠ ግድግዳ የሚመረግበትን ጭቃ ከጭድ ጋር አዋህዶ አቦካ።

ጭቃ ረጋጭ / አቡኪ ስ ለምርግ ስራ ተስማሚነት ያለውን አፈር በውሃ እያሳቆጠና ከጭድ ጋር እያቀላቀለ እስኪቦካ ድረስ በመርገጥ የቤት ግድግዳን የሚመርግ ባለሙያ።

[የ] ጭቃ ሱሪ ስ በክረምት ወይም በጭቃ ጊዜ የሚለበስ አጭር ሱሪ።

የጭቃ እሾህ ሳይታወቅበት በስውር የሚያጠቃ ወይም የሚጎዳ+ ተንኮለኛ (ሰው)።

[የ] ጭቃ ጅራፍ የሚያስቀይም ወይም የሚያስከፋ ንግግር (ሳይጠብቁት የተነገረ)።

ጭቃ ሹም ስ በቀድሞ ስርአት የመሬት ስሪት ውስጥ በየአካባቢው በህዝብ ተመርጦ፥ ከአጥቢያ ዳኛና ከመልከኛ በታች እንደ መንግስት ሹም ሆኖ የሚያገለግል ሰው።

ጭቃ ቀለም ስ የሰደለደ ቀለም ያለው መገፊያ፣ እስኪርቢቶ።

ጭቃ ቅባት ስ ፈሳሽ ያልሆነ ቅባት።

ጭቃ ቤት ስ ግድግዳው በእንጨት ተሰርቶ በጭቃ የተመረገ ቤት (የሸክላ፥ ወይም የድንጋይ ቤት ያልሆነ)።

ጭቃ አፍ ቅ ሲሳደብ ለአፉ ለከት የሌለው፥ ተሳዳቢ።

ጨቀጨቀ¹ ግ 1. ነዘነዘ+ ወተወተ+ ነተረከ፥

በነገር አሰለቸ። 2. ጠቀጠቀ፥ ደፈነ፥ ወተፈ። 3. መላልሶ ወጋ (በጦር፥ በሹል ነገር፥...)። 4. እርጥብ ጌሾን፡ ቃሪያን፥ በቆሎን፥... ወቀጠ።

መጨቅጨቂት (መጨቅጨቂያ) ስ እንጀራ ሲጋገር እንዳይነፍስበት በአክንባሎና በምጣድ መሃል ያለውን ቀዳዳ ለመድፈን በውሃ እየተራሰ የሚጠቀጠቅ የጨርቅ ትልታይ።

ጨቅጫቃ ቅ ነዝናዛ፥ ነትራካ፥ በነገር የሚያሰለች።

ጭቅጭቅ ስ 1. ንዝንዝ፥ ንትርክ። 2. ጠብ፥ አለመስማማት። 3. ሙግት፥ የፍርድ ቤት ነገር።

ጭቅጭቀኛ ቅ ተነዛናዥ፥ ተነታራኪ።

ተጨቃጨቀ ግ 1. ተነዛነዘ፥ተነታረከ። 2. ተከራከረ፥ ተሟገተ፥ ተጣላ።

ተጨቃጫቂ ቅ ተነዛናዥ፥ ተነታራኪ፥ ጭቅጭቅ የማይሰለቸው።

አጨቃጨቀ ግ አጣላ፥ አወዛገበ፥ አነታረከ።

አጨቃጫቂ ቅ አወዛጋቢ፥ የሚያጣላ፥ የሚያነታርክ፥ አከራካሪ የሆነ(ነገር፥ ንብረት፥...)።

ጨቀጨቀ² ግ ጨቀየ፥ በዝናብ ወይም በውሃ ራሰ።

ጨቀጨቅ ስ ውሃ ያለበት ጭቃማ መሬት።

ጨቅሳ ስ 1. አራስ፥ ሊጋ፥ ሰውነቱ ያልጠነከረ፥ ርጥብ ህፃን፥ ልጅ። 2. (ዘይ.) አስተሳሰቡ ያልበሰለ፥ እርቆ የማያስብ፥ የማያስተውል።

ጨቅጫቃ "**ጨቀጨቀ¹**" ስር ተመ.

ጨቆነ ግ 1. ተጫነ፥ ገፍቶ፥ ረግጦ፥ አጣብቆ ያዘ። 2. በአገዛዙ ወይም በሃላፊነቱ በደለ፥ ግፍ ፈፀመ፥ አሰቃየ፥ መብት ገፈፈ።

ጨቋኝ ቅ ግፍ ሰሪ ፡ በዳይ፥ መብት የሚነፍግ (በአስተዳደር፥ በአገዛዝ)።

ጭቁን ቅ መብቱና ነፃነቱ የተገፈፈ፥ በደል፥ ስቃይ የደረሰበት።

ጭቆና ስ 1. መብትን፥ ነፃነትን የመግፈፍና የማሰቃየት ድርጊት። 2. የመጨቆን፥ መብት የማጣት ወይም የመከልከል ሁኔታ።

ተጨቆነ ግ ተሰቃየ፥ ግፍ ተሰራበት፥ በደል ተፈፀመበት፥ መብቱ ተገፈፈ(በአስተዳደር፥ በአገዛዝ፥...)።

ተጨቋኝ ቅ በደል፥ ስቃይ፥ ግፍ የደረሰበት (ሰው)።

***ጨበረረ**

ጨበረር (ጨብራራ) ቅ የተንጨበረረ፥ የተንጨፈረረ፥ ያልተበጠረ (ፀጉር)።

ጨበሬ ቅ የተንጨበረረ፥ የተንጨፈረረ፥ የቆመ፥ ያልተበጠረ(ፀጉር)።

ተንጨበረረ ግ ተንጨፈረረ፥ ቆመ (ፀጉር)።

አንጨበረረ ግ አንጨፈረረ፥ አነፈረ፥ አቆመ (ፀጉርን) ።

እንጭብሬ ስ ራስ ብትን ዘንጋዳ።

***ጨበረበረ**

ተጭበረበረ ግ ተታለለ።

አጭበረበረ ግ አታለለ፥ አሳሳተ፥ አደናገረ።

አጭበርባሪ ቅ አታላይ፥ አወናባጅ።

ጨበሬ¹ ስ ቀይነት ያለው አፈር።

ጨበሬ² "***ጨበረረ**" ስር ተመ.

***ጨበሰበሰ**

ጨበስባሳ ቅ በጭስ፥ በበሽታ፥... የተጭበሰበሰ፥ የተጨናበሰ፥ ሞጭሟጫ (አይን)።

ተጭበሰበሰ ግ 1. ተጭፈነፈነ፥ በደንብ አላይ አለ (አይን)። 2. በደንብ አልነድ አለ፥ ጨሰ (እርጥብ እንጨት)።

አጭበሰበሰ ግ አጭፈነፈነ፥ አሳሳይ አለ (አይንን፥...)።

ጨበጠ ግ 1. እጁን ከሌላ ሰው እጅ ጋር በማያያዝ ሰላምታ ሰጠ ወይም ሰላምታ ተለዋወጠ። 2.ያዘ፥ የራሱ አደረገ። *ስልጣን መንግስት ጨበጠ።* 3. ጭብጦ አዘጋጀ። 4. አንድን ነገር በጣቶቹና በመዳፉ አስገብቶ ያዘ። 5. ጣቶቹን ኮርምቶ በመዳፉ ላይ ያዘ ወይም ለቡጢ መምቻ እንዲሆን አደረገ። 6. ዋጋውን አስወደደ። *ነጋዴው የሚሸጥበትን ዋጋ ጨበጠ።* 7. ጉዳዩን አሰረ ያዘ፥ እንዳይፈፀም አደረገ። *ጉዳዩ እንዳይፈፀም የጨበጠብኝ ጉቦ ፈልጎ ነው።* 8. ኮረመተ፥ አሰረ፥ አሰቃየ (ብርድ፥ ረሃብ፥ በሽታ፥ ችግር፥...)። *ብርዱ ሰውነቱን ጨብጦታል።* 9. አወቀ፥ ተረዳ፥ ያዘ(ጉዳይን፥ ነገርን፥...)።*ፍሬ ሃሳቡን ጨብጦታል።* 10. (ዘይ.) አስቀመጠ፥ አጠራቀመ፥ ያዘ (ሃብትን፥ ንብረትን፥...)።

መጨበጫ ስ የአንድ ነገር መያዣ ወይም እጀታ፥ በእጅ አጥብቆ ለመያዝ አመቺነት ያለው የአንድ ነገር አካል።

መጨበጫ የለውም 1.በግልፅ አይታወቅም፥ ዝብርቅርቅ ነው፥ አይያዝም (ሃሳቡ፥ ፍላጎቱ፥...)። 2.ለመያዝ አያመችም።

ጨበጣ (የጨበጣ ውጊያ) ስ በሳንጃ ወይም በሰደፍ ወይም በሌላ በእጅ የሚያዝ መሳሪያ በመጠቀም አጠገብ ለአጠገብ ሆኖ ግብግብ የሚጋጠሙበት ውጊያ።

ጨባጣ ቅ (ስድብ) 1. ክርማታ፥ አጭርና ቀጭን። 2. በህመም ምክንያት አካሉ የተኮራመተ (ሰው)።

ጨባጭ ቅ ንፉግ፥ ሰስታም።

ጭብጥ ስ የአንድ ነገር ወይም ጉዳይ ፍሬ ሃሳብ።

ጭብጡን አፈሰሰ ጭብጡን ለመስካሪ ነገረ ወይም ገለጠ፣ አስረዳ።

ጭብጥ ስ 1. የተጨበጠ እጅ፣ ኩርኩም፣ ቡጢ፣ ጡጫ። 2. በአንድ እጅ መዳፍ ውስጥ የተጨበጠ (ጥሬ፣ ብር፣...)። 3. ትንሽ ወይም ጥቂት ነገር። *ጭብጥ ቆሎ ይዞ ወደ ላሽር ሄደ።*

ጭብጦ ስ 1. ተጋግሮ በትኩሱ የተድበለበለ እንጀራ (የመንገደኛ ስንቅ)። 2. ከበሶና ከማር ተድቦልቡሎ የተዘጋጀ ምግብ፣ ስንቅ።

ተጨበጠ ግ 1. ተያዘ፣ ተገኘ፣ ታወቀ። *ሃሳቡ ተጨብጦልኛል።* 2. ተኮራመተ፣ ታሰረ (በሃዘን፣ በበሽታ፣...)።

የተጨበጠ በግልፅ የታወቀ፣ የተረጋገጠ።

ተጨባጭ ቅ በእርግጥ ያለ፣ የሚኖር ወይም በአካል የሚገኝ (ለነገር፣ ለክስተት፣ ለአካላዊ ነገር)።

ተጨባጭ ሁኔታ ስ አንድን ነገር እስመልክቶ በአንድ ወቅት የሚታየው ወይም ያለው ነባራዊ (ትክክለኛው) ሁኔታ ወይም ነገር።

ተጨባበጠ ግ 1. ተኮራመተ። 2. ተጣጠፈ፣ ተጨማደደ። 3. የእጅ ሰላምታ ተለዋወጠ፣ እጅ ለእጅ ተያያዘ።

አጨባበጠ ግ በእጅ ማጨባበጥ አማካይነት አስማማ፣ አስታረቀ።

አስጨበጠ ግ 1. የጉዳዩን ፍሬ ሃሳብ ወይም ቁም ነገር አስያዘ፣ አስረዳ። 2. ሰጠ፣ በእጁ እንዲይዝ አደረገ።

ጨበጨበ ግ ለመለመ፣ አቆጠቆጠ፣ ቅጠል አወጣ።

አጨበጨበ ዝ.ከ.

***ጨበጨበ**

ጭብጨባ ስ ሁለት ውስጥ እጆችን በማማታት የሚፈጠር ድምፅ (ዘፈንን፣ ሰቅሰን ለማድመቅ፣ ደስታን፣ ስምምነትን ለመግለፅ እንዲሁም ለመጣራት የሚደረግ)።

ተጨበጨበ ግ ጭብጨባ ተደረገ።

አጨበጨበ ግ 1. ሁለት ውስጥ እጆችን አማታ፣ አጣፋ፣ ቸብቸብ አደረገ። 2. ነገር አዳነቀ፣ አቶከቶከ።

አጨበጨበበት ተደሰተበት፣ ተዝናናበት፣ ጠጣበት፣ ጨፈረበት (ገንዘቡን)።

አጨብጭቦ ቀረ ምንም ሳያገኝ ባዶ እጁን ቀረ።

አጨብጭቦ ተቀበለ በደስታ ተቀበለ።

አጨብጫቢ ቅ ነገር አዳናቂ፣ አቶክቷኪ፣ አጎብጓቢ።

አስጨበጨበ ግ አድናቆትን አገኘ ወይም አተረፈ ደስ አሰኘ።

ጨቡዴ "ጨቦደ" ስር ተመ.

ጨባ ስ ከሰል የሚሆን ወይም የወተት ማእጠንት የሚያደርጉት የግራር አይነት።

ጨባጣ "ጨበጠ" ስር ተመ.

ጨባጭ ዝ.ከ.

ጨብራራ "*ጨበረረ" ስር ተመ.

ጨብጥ(ጨብጦ) ስ ሽንት የሚከለክልና የሚያቃጥል የአባለ ዘር በሽታ።

ጨቦደ ግ አጥብቆ ያዘ፣ ጨበጠ፣ አፈፍ አደረገ።

ጨቡዴ ቅ ሃይለኛ፣ ጠንካራ፣ ጉልበተኛ (ሰው)።

ጨነቀ ግ ቸገረ፣ አወከ። *ለበሽታው መድሃኒት ለማግ ጨነቀው።*

ጨነቀኝ ጠበበኝ ቸገረኝ፣ የማደርገውን አጣሁ፣ ተሰቃየሁ።

ጭንቅ ስ ችግር፣ ስቃይ፣ መከራ፣ ፍርሃት።

የጭንቅ አማላጅዋ ስ የቅድስት ማርያም የቅፅል ስም።

ጭንቀት ስ በህመም በልዩ ልዩ ችግር ምክንያት አእምሮን፣ የሚያሰቃይ፣ የሚረብሽ ወይም በጣም የሚያሳስብ መጥፎ ስሜት።

ጭንቀታም ቅ ፈሪ፣ በሆነው ባልሆነው ጭንቀት ወይም ፍርሃት የሚያበዛ።

ተጨነቀ ግ ተቸገረ፣ ተጠበበ፣ ታወከ፣ ተሰቃየ፣ የሚያደርገውን አጣ፣ ግራ ተጋባ (በህመም፣ በችግር፣ በሃሳብ፣...)።

ተጨናነቀ ግ በጣም ተጣበበ፣ ተጠጋጋ፣ ተደራረበ፣ አላፈናፍን አለ።

አጨናነቀ ግ በጣም አጠጋጋ፣ አደራረበ፣ አጣበበ።

አስጨነቀ ግ አስቸገረ፣ መፈናፈኛ ከለከለ።

ጨነቆረ ግ 1. አንድ አይኑን ጨፍኖ አየ ወይም ተመለከተ። 2. በቀዳዳ አየ። 3. የተጨናቆረ ወይም የተጭፈነፈነ ፅሁፍ ፃፈ፣ ቦጫጨረ።

ጨንቋራ(ጭንቁር) ቅ ጨምባሳ(ለአይን)።

ጭንቁርቁር ቅ 1. ጭምብስብስ። 2. በደንብ የማይነበብ፣ የተቦጫጨረ (ፅሁፍ)።

ተጨናቆረ ግ (ለፅህፈት) የማይነበብ ሆነ፣ ተቦጫጨረ።

***ጨነበሰ**

ጨንባሳ (ጨምባሳ) ቅ 1. በደንብ የማይነድ፣ የሚጨስ (እሳት)። 2. የተጨናበሰ፣ በደንብ የማያይ (አይን)።

ጭንብስብስ ቅ የተጨናበሰ፣ በደንብ የማያይ (አይን)።

ተጨናበሰ ግ 1. በደንብ የማያይ ሆነ፣

ተጨናቆረ፣ ተጭፈነፈነ። 2. በጭስ ታፈነ፣ ታወከ።

አጨናበሰ ገ ማየት አወከ፣ አስቸገረ(አይንን)።

ጨንገዘ ገ ቆረጠ፣ ቀረደደ፣ አጨደ።

ጨነገፈ ገ 1. ፅንሱ ከመወለጃ ጊዜው ቀደም ብሎ ህይወት አልባ ሆኖ ወጣ። 2. (የተተኮሰ ጥይት) ተበላሸ፣ ከሸፈ፣...። 3. የታሰመ፣ የታቀደው ጉዳይ ሳይሳካ ቀረ፣ ተጓጎለ፣ ተሰናከለ።

ጨነገፈች ገ አስወረደች፣ ቀኑ ሳይደርስ ህይወት የሌለው ፅንስ ከማህፀኗ ወጣ።

ጭንጋፍ ቅ (ስድብ) 1. ያለ ቀኑ የተወለደ። 2. ጨባጣ፣ ድውይ፣ኮስማና። ስ 3. ሞቶ የወጣ ፅንስ፣ ሽል።

ተጨናገፈ ገ ተጓጎለ፣ ከሸፈ፣ ተሰናከለ (የታቀደ፣ የተጀመረ ስራ ወይም ሌላ ነገር)።

አጨናገፈ ገ አስተጓጎለ፣ አከሸፈ፣ አሰናከለ፣ አደናቀፈ።

አስጨነገፈ ገ ፅንሱ ህይወት አልባ ወይም ውርጃ ሆኖ እንዲወጣ አደረገ (በሽታ ወይም ሌላ ችግር)።

***ጨነጎለ**

ጨንጓላ ቅ የተሰናከለ፣ አጓጉል የቀረ፣ ለውጤት ያልበቃ።

ተጨናጎለ ገ ተጓጎለ፣ ተሰናከለ፣ ለውጤት ሳይበቃ ቀረ።

አጨናጎለ ገ አሰናከለ፣ አጓጉል አደረገ፣ ያለውጤት አስቀረ።

***ጨነፈረ**

አጨናፈረ ገ መታ፣ ክፉኛ አሳመመ። *ምች አጨናፍሮ ጣለው።*

ጨንቋራ **"ጨንቆረ"** ስር ተመ.

ጨንባሳ **"*ጨነበሰ"** ስር ተመ.

ጨንገር ስ 1. ልምጭ፣ አርጩሜ፣ ለበቅ። 2. አገዳው ቀጥ ብሎ የሚወጣ የጤፍ አይነት።

ጨንጓላ **"*ጨነጎለ"** ስር ተመ.

ጨከነ ገ 1. ክፉ ሆነ፣ ከርህራሄ፣ ከሃዘኔታ ራቀ። 2. ቻለ፣ ታገሰ፣ በረታ፣ ደፈረ። 3. ቆረጠ፣ ሳያመነታ ቀረ። *ጨክና ሄደ።*

ጨካኝ ቅ ርህራሄ ወይም ሃዘኔታ የሌለው።

ጭካኔ ስ 1. ክፉት፣ ርህራሄ፣ ሃዘኔታ የሌለበት ስሜት። 2. ብርታት፣ ድፍረት፣ ትእግስት።

ጨከከ ገ አረጀ፣ ጨረጨሰ (ለሰው)።

ጨከከች ገ ቁፍ፣ ጭር አለች። *ዶሮዋ ሃያ አምስት እንቁላል ከወለደች በኋላ ጨከከች።*

ጨካካ ቅ 1. ያረጀ፣ የጨረጨሰ (ሰው)። 2. ቁፍ፣ ጭር ያለች (ዶሮ)።

ጨካኝ **"ጨከነ"** ስር ተመ.

ጨካካ **"ጨከከ"** ስር ተመ.

***ጨወተ**

ጨዋታ(ጫወታ) ስ 1. ንግግር፣ ውይይት። 2. ልፊያ፣ ድሪያ፣ ቀልድ። 3. የሚያስቅ፣ የሚያዝናና ወሬ ወይም ንግግር። 4. ውድድር ወይም ፉክክር ያለበትና የሌለበት የቤትና የውጪ ስፖርት፣ መዝናኛ፣ ሌላም አይነት እንቅስቃሴ። 5. ዘፈን፣ ዳንስ፣ ውዝዋዜ፣...።

ጨዋታ ፈረሰ ጨዋታው አበቃ፣ አቆመ። *ጨዋታ ፈረሰ ዳቦ ተቆረሰ።*

ከጨዋታ ውጭ (ስፖ.) በእግር ኳስ ጨዋታ ላይ ከሚፈፀሙና ቅጣት ከሚያስጡ ስህተቶች አንዱ።

የጨዋታ የቀልድ፣ የምር ያልሆነ።

ጭውውት ስ ወሬ፣ የርስ በርስ ውይይት ወይም ንግግር።

ተጫወተ ገ 1. ተነጋገረ፣ ተወያየ። 2. ተላፋ፣ ተቃለደ። 3. የጨዋታ ወይም የውድድር እንቅስቃሴ አደረገ። 4. ዘፈነ፣ ጨፈረ።

ተጫወተበት 1.ጉድ ሰራው፣ ያሳሰበውን ነገር ፈፀመበት። 2 . ቀለደበት፣ አሾፈበት። 3. አላግባብ ተጠቀመ። *ገንዘቡን ተጫወተበት።*

መጫወቻ ስ 1. እንደ ኳስና አሻንጉሊት ያለ ለጨዋታ የሚያገለግል እቃ። 2. መቀለጃ፣ ማሾፊያ። *አንበሳ ሲያረጅ የዝንብ መጫወቻ ይሆናል።* 3. እንደ ክራር፣ ማሲንቆ፣ ዳማ፣ ካርታ የመሳሰሉ እቃዎች ወይም መሳሪያዎች።

ተጫዋች ቅ 1. ቀልደኛ፣ ጨዋታ አዋቂ። 2. በእግር ኳስ፣ በመረብ ኳስ ወይም በሌላ አይነት ጨዋታ የሚሳተፍ።

አጫወተ ገ 1. አነጋገረ፣ አወያየ። *እንግዳውን አጫወተው።* 2. አባበለ፣ እንዳያለቅስ አደረገ (ህፃንን) ። 3. (ስፖ.) በዳኝነት መራ። *እግር ኳስ ያጫወት የነበረው ዳኛ ታመመ።* 4. በጨዋታ እንዲሳተፍ አደረገ፣ ፈቀደ፣ አስገባ። *ኳስ የሚጫወቱት ልጆች አጫውቱኝ ብላቸው እንቢ አሉኝ።*

ማጫወቻ ስ ልጅ እንዳያለቅስ ማባበያ ወይም ማታለያ የሚሆን ልዩ ልዩ እቃ።

አጫዋች ስ 1. የሚያነጋግር፣ የሚያወያይ፣ የሚያዝናና ቀልድ አዋቂ ሰው። 2. (ስፖ.) የእግር ኳስ ወይም የሌላ ስፖርታዊ ውድድር ዳኛ።

ጨዋ ስ 1. በግብሩ ወይም በጠባዩ ጥሩ ስነ ምግባር ያለው፣ ከአፀያፊ ተግባር የራቀ(ሰው)። 2. ያልተማረ፣ ማይም።

ጨዋታ **"*ጨወተ"** ስር ተመ.

ጨው ስ ምግብ ጥሩ ጣእም እንዲያገኝና ሳይበላሽ እንዲቆይ ለማድረግ የሚያገለግልና ከመሬት ወይም ከውሃ የሚገኝ ነጭ ማእድን ፤ ሻሸቦ ::

ጨው ሆነ 1. ተወደደ:: 2. ሟሟ::

ጨው መሰለ ነጫጭባ ሆነ::

ጨው ጨው አለ የጨው ወይም የመኮምጠጥ ጣእም ሰጠ::

ጨደደ ግ 1. ቀደደ፤ ሰነጠቀ:: 2. ከበበ::

ጨገሬታ(ጭገሬታ) ስ ዱካ፥ ደብዛ፥ ምልክት:: *የሌባው ጨገሬታ ጠፍቷል::*

ጨገገ ግ 1. ጨለመ፥ ጭጋግ ሆነ:: 2. ከበደ፥ ጨፈገገ::

ጭጋግ ስ አቧራ የተሸከመ ወይም ጉም የሚመስል አየር::

ጭጋግ ፊት የከፋው የሚመስል (ሰው)::

አጨገገ ግ አጨፈገገ፥ አከፋ(ፊትን)::

ጨጎረ ግ 1. ፀጉር አወጣ ወይም አበቀለ(ሰውነት):: 2. አረም አበቀለ (መሬት)::

ጭገር ስ በሰዎች ብብትና አባለ ዘር አካባቢ የሚበቅል ፀጉር፤ ጭጉኝ::

ጭገሩ ቆመ ነገር ነገር አለው::

ጭገራም ቅ ብዙ ፀጉር ያለው::

አጨጎረ (አጨገረ) ግ 1. ሰውነቱ ፀጉር አወጣ ወይም አበቀለ:: 2. አረም አበቀለ::

ጨጓራ ስ በሰውና በእንስሳት ሆድ የሚገኝ፥ ለምግብ መፍጫነት የሚያገለግል እንደ ከረጢት ያለ አካል::

የጨጓራ በሽታ ስ በጨጓራ ውስጠኛ አካል ላይ የሚሰማ ህመም::

ጨጓራ ፊት ቅ 1.በኩፍኝ ወይም በፈንጣጣ ምክንያት ፊቱ የተበላሸና ጠቃጠቆ ያለበት:: 2. ጭፍግግ ያለ፤ የተከፋ የሚመስል::

ጨጨብሳ ስ ተሰባብሮ በቅቤ የታሸ ቂጣ::

ጨሮ(ሮሮ) ስ በወይና ደጋ የሚበቅልና ሲነድ እየተንጣጣ የሚፈናጠር የቁጥቋጦ አይነት ::

ጨፈለቀ ግ 1. ረገጠ፤ ጻጠ፡ ደፈጠጠ:: 2. ለየብቻ የነበረውን አንድ ላይ አደረገ፤ አቀላቀለ:: *ወርቆቹን ካልጨፈለቁ ለአንገቷ ሃብል አይሰራም::* 3. ገመሰ፥ ተረተረ፡ ሰነጠቀ ወይም የመጀመሪያውን እርሻ አረሰ ::

ጭፍልቅ ቅ የመጀመሪያ እርሻ::

ተጨፈለቀ ግ 1. ለየብቻ የነበረው አንድ ላይ ተደረገ፤ ተቀላቀለ፥ ተዋሃደ:: 2. ተገመሰ፥ ተሰነጠቀ፥ የመጀመሪያው እርሻ ተከናወነ::

ጨፈረ ግ 1. በአመት በአል፥ በሰርግ፥ በልዩ ልዩ ደስታ ቀን፡... እየዘፈኑ ዘለለ፥ በአንገት ወረደ፥ ተወዘወዘ:: 2. (ዘይ.) በረቀ፡ ተደሰተ:: 3. (ዘይ.) በንዴት ወይም በቁጣ ብዙ ተናገረ::

ጭፈራ ስ ዝላይ፥ ዳንኪራ፥ ውዝዋዜ (የደስታ፥ የፈንጠዝያ)::

ጭፉሮ ዝ.ክ::

ተጨፈረ ግ ጭፈራ ተደረገ::

ተጫፈረ ግ ተጣመረ፥ በአጫፋሪ ምእላድ ተያያዘ::

አጫፈረ ግ (ሰዋ.) አገናኘ፥ አጣመረ/ለምሳሌ ወንድሙና እህቱ ነገ ይመጣሉ በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ "ና" አጫፋሪ ነው፤ ወይም ወንድሙ፥ እህቱ፥ አክስቱም ነገ ይመጣሉ በሚለው አረፍተ ነገር ውስጥ "ም" አጫፋሪ ነው)::

አጫፋሪ ቅ 1. አበር፥ ግብረ አበር፥ አብሮ የሚሄድ፥ደጋፊ:: ስ 2. አያያዥ ወይም አጣማሪ ምእላድ::

አስጨፈረ ግ 1. እንዲዘፈን፥ እንዲጨፍር አደረገ:: 2. አስደሰተ:: 3. አናደደ፥ አበሳጨ፥ አስቆጣ::

***ጨፈረረ**

ጨፍራራ (ጨፈረር) ቅ በቅጡ ያልተበጠረ (ፀጉር)::

ጭፍርር አለ ግ 1. በጣም ተንጨፈረረ፥ ቆመ(ፀጉር):: 2. ደረቀ (እፅዋት):: 3. (ዘይ.) ሞተ፥ ተፈነቸረ::

ተንጨፈረረ ግ 1. ተንጨበረረ (ፀጉር::) 2. ዛፍ ከድርቅ የተነሳ ቅጠሉቹን አራግፎ እንጨቱ ብቻ ቀረ:: 3. (ዘይ.) ሞተ::

አንጨፈረረ ግ 1. ፀጉር ከተገቢው በላይ በማደግ ወይም በጣም ባለመያዙና ባለመበጠሩ ደርቆና ቀጥ ብሎ እንዲቆም ወይም ደግሞ ስርአት ባጣ መልኩ እንዲመሰቃቀልና እንዲንጨበረር አደረገ 2. ወደ ላይ አቆመ፥ ዘረጋ::*እጁን አንጨፍሮ ጌታዬ ጌታዬ እያለ ይማጠን ነበር::*

ጨፈቀ ግ 1. ለሰቀ፤ ለጥ ቀጥ አደረገ(ጨፈቃ ላይ ከባድ ነገር በማስቀመጥ፥ በመጫን፥በመርገጥ):: 2. መታ፥ ደበደበ:: 3. አጠጋጋ፥ ጠቀጠቀ::

ጨፈቃ ስ ትንንሽ ቅርንጫፍ ያለው ቀጫጭን እንጨት (ለቤት ግድግዳ ለአጥር፥... ስራ የሚያገለግል)::

ተጨፈቀ ግ በጨፈቃው ላይ ከባድ ነገር ተጭኖበት ልሰቅ እንዲል ተደረገ::

ጨፈነ ግ 1. አይኑን ከደነ፥ ገጠመ:: 2. ደበዘዘ፥ ብርሃን ጠፋ (በጉምና በዝናብ ምክንያት)::

ጨፋና ቅ አይኑ በደንብ የማይገለጥ ወይም የማያይ (ሰው)::

ጭፍን ቅ 1. የታወረ ወይም የማያይ (አይን):: 2. ግልፅ ያልሆነ:: 3. የማያመዛዝን ወይም የማያስተውል:: 4. በቂ ምክንያት የሌለው ወይም ያልታሰበበት:: *ጭፍን የአሰራር እርምጃ::*

በጭፍን በመላ፣ ሳይመራመሩ፤ በድፍረት።

ጭፍንፍን ቅ ጨለማ የሆነ።

ተጨፈነ ግ ተገጠመ፣ ተከደነ፣ ተሸፈነ(አይን)።

ተጭፈነፈነ ግ 1.አየሩ በጉም፣ በጭጋግ ተሸፈነ፣ ጨለማ ሆነ። 2. ተድበሰበሰ፣ ግልፅ ሳይሆን ቀረ።

ጨፈገገ ግ 1. ከበደ፣ ጠቆረ (የአየር ሁኔታ)። 2. (ዘይ.) ፊቱን አጠቆረ፣ አጨማደደ።

ጨፍጋጋ ቅ 1. የጠቆረ፣ የከበደ(የአየር ሁኔታ)። 2. (ዘይ.) የማይጠዳው፣ ፊቱ የከበደ፣ የተከፋ የሚመስል።

ጭፍግግ ዝ.ከ. ።

ጭፍግግ አለ ግ ጠቆረ፣ ከበደ (አየሩ)።

ጭፍግግ አደረገ ግ አጨማደደ፣ አኮሳተረ(ፊቱን)።

ጨፈጨፈ[1] ግ 1. ቁጥቋጦን፣ ቅጠላቅጠልን፣... በስለት ወይም በመጥረቢያ፣... መለመለ፣ መነጠረ። 2. በዱላ፣ በመጥረቢያ፣...መታ፣ ደበደበ፣ ከተከተ። 3. በጣም ሰደበ፣ ዘለፈ። 4. በብዛት ገደለ፣ ፈጀ፣ ጨረሰ።

ጨፍጫፊ ቅ ጨካኝ፣ አረመኔ፣ ህዝብን የሚፈጅ።

ጭፍጨፋ ስ 1. የጅምላ ፍጅት፣ ግድያ። 2. እፅዋትን የመቁረጥና የማጥፋት ድርጊት።

ጭፍጫፊ ስ 1. ቁርጥራጭ፣ ትርፍራፊ (የእንጨት፣ የነገር)።2. ከነገሩ ጋር የተያያዘ ነገር ግን እንደ ዋና ፍሬ ነገር የማይወሰድ ነጥብ ወይም ሃሳብ።

ተጨፈጨፈ ግ 1. ተመነጠረ(ዛፍ፣ሳር፣ቅጠል፣...)። 2 በብዛት ተገደለ (ሰው)። 3. (ዘይ.) ተሰደበ፣ ተዘለፈ።

ጨፈጨፈ[2] ግ አጠበ (ልብስን)።

ጨፈጨፍ ስ እግር የሚቆራርጥና የሚሰነጣጥቅ የክረምት ጭቃና ውሃ።

ተንጨፈጨፈ ግ 1. ተንቸረፈፈ፣ ወዛ። *የፊቱ ወዝ ተንጨፈጨፈ።* 2. ታጠበ፣ ተለቀለቀ (ልብስ)።

እንጨፈጨፈ ግ 1. አጠበ፣ አፀዳ፣ አለቀለቀ (ልብስን) 2. (ዘይ.) ሰደበ። *በስድብ አንጨፈጨፈው።*

እንጭፍጫፊ ስ የልብስ እጣቢ።

ጨፋና "**ጨፈነ**" ስር ተመ.

ጨፌ ስ 1. ለምለም ሳር የሚበቅልበት ሁሣማ መሬት። 2. ውሃ ባለበት መሬት ላይና በወንዝ ዳር የሚበቅል ረጃጅም የሆነ ለምለም ሳር።

ጨፍራራ "***ጨፈረረ**" ስር ተመ.

ጨፍጋጋ "**ጨፈገገ**" ስር ተመ.

ጨፍጫፊ "**ጨፈጨፈ**[1] " ስር ተመ.

ጩ የ"**ጨ**" ፊደል ካእብ ዘር።

ጩሀት " **ጮሀ**" ስር ተመ.

ጩልፋት "**ጨለፈ**" ስር"**ጭለፋት**"ን ተመ.

ጩልጩል

ጩልጩሌ ቅ አይኑ ትንንሽ።

ጩልጩል አለ ግ ክፍት ክድን አለ (ትንሽ አይን)።

ጩርር

ጩርር አለ ግ 1. ሆድ በህመም ወይም በመታወክ ምክንያት ጮሀ። 2. ውሃ ሲንቆረቆር የሚሰጠውን አይነት ድምፅ ሰጠ ወይም አሰማ።

ጩቅ ቅ ስስታም፣ ገብጋባ።

ጩቤ ስ እንደ ቢላዋ ያለ ሆኖ ከአንድ ወይም ከሁለት በኩል ስለት ያለውና በወገብ ላይ የሚታጠቁት የጦር መሳሪያ።



ጩቤ

ጩጬ ስ 1 የወፍ አይነት። 2 (ዘይ.) በጣም ትንሽ ልጅ (ተራ. አነ.)።

ጪ የ "**ጨ**" ፊደል ሳልስ ዘር።

ጪሰኛ "**ጨሰ**" ስር ተመ.

ጪስ ዝ.ከ

ጫ[1] የ"**ጨ**" ፊደል ራብእ ዘር።

ጫ[2]

ጫ አለ ግ እረጭ፣ ፀጥ አለ።

ጫማ ስ 1. ከቁርጭምጭሚት በታች ከተረከዝ እስከ ጣት ድረስ ያለውና መሬት መርገጫ የሆነው የሰውነት ክፍል። 2. ከቆዳ ወይም ከፕላስቲክ ወይም ከሸራ የተሰራ በእግር የሚጠለቅ የእግር መርገጫ፤ መጫሚያ። 3. የቁመት፣ የከፍታ፣ የርቀት መጠን መለኪያ (አንድ ጫማ መጠኑ 0.305 ሜትር ነው)።



ጫማ

ጫማ ላሰ/ሳመ ተለማመጠ።

ጫማ አደረገ ጫማን በእግሩ አጠለቀ።

ጫማውን ጨረሰ አንድን ጉዳይ ለመፈፀም፣... ያለመሰልቸት ደከመ፣ ተመላለሰ።

የጫማ ማሰሪያ ስ ጫማ ከእግር ላይ እንዳይወልቅ የሚታሰርበት ወፈር ያለ ክር፣ ሲር።

የጫማ ማንኪያ ስ ጫማን ለማጥለቅ የሚረዳ ከቀንድ ወይም ከፕላስቲክ፣... የሚሰራ እቃ።

የጫማ ምላስ ስ ፊት ለፊት በጫማ ክር ማሰሪያዎች መካከል ያለውን ክፍት ቦታ የሚሸፍን ስስ ቆዳ።

የጫማ ቀለም ስ ቆዳ ነክ የሆነ ጫማን ለማለስለስና ለማሳመር የሚያገለግል ቅባትነት ያለው ቀለም።

የጫማ ቡርሽ ስ ጫማን ቀለም ለመቀባትና ለመወልወል የሚያገለግል ቡርሽ።

ጫማ ሰፊ ስ ጫማን በልክ ወይም በእግር መጠን (ቁጥር) የሚሰፋ ወይም የተቀደደውን የሚጠግን ባለሙያ።

ጫማ ጠራጊ ስ ጫማን በመወልወልና በማሳመር በሚያገኘው ገቢ የሚተዳደር ሰራተኛ፤ ሊስትሮም ይባላል።

ተጫማ ግ ጫማ አደረገ።

መጫሚያ የ"**ጫማ**"ን 1ኛና 2ኛ ፍቺ ተመ.

ጫረ ግ 1. እሳትን ከምድጃ ውስጥ በገል ወይም በሌላ ነገር ዝቆ አወጣ። 2. የክብሪትን እንጨት ራስና በክብሪት ቤቱ ጎን ላይ ያለውን ሻካራ ክፍል በማፋተግ እሳት አወጣ። 3. ጋሬጣ፣ እንጨት፣ ምላጭ፣... የሰውነትን ክፍል ወይም የሌላን ነገር አካል በመጠኑ ሰነጠቀ ፤ ቧጨረ፣ ፋቀ። 4. መሬትን በትንሹ ቆፈረ። *ዶሮ እየጫረች ትበላለች።* 5. (የግ.አነ.) ፃፈ። 6 (ዘይ.) ጀመረ፣ ተነኮሰ (ነገርን፣ ጠብን)።

መጫሪያ ስ 1. የእሳት መውሰጃ ገል። 2. ቆሻሻ ለመሰብሰብ የሚያገለግል የተቆለመመ ጥርሶችና ረጅም እጀታ ያለው የእርሻ መሳሪያ።



መጫሪያ

ጭረት ስ እንደ ሰረዝ ያለ ምልክት። 2. ከሆሄያት የዜማ ምልክቶች አንዱ፤ ምልክቱም (\) ነው ።

ተጫረ ግ አንድ አካል ወይም የሰውነት ክፍል ተቧጨረ ፣ ተሸነተረ፣ ተፋቀ (በጋሬጣ ፣ በእንጨት፣...)።

ተጫጫረ ግ 1. ብዙ ቦታ ላይ ተቧጨረ፣ ተሸነታተረ፣ ተፋፋቀ። 2. አንዱ ከሌላው ቤት እሳት ወሰደ።

አጫረ ግ ተነኮሰ፣ ጀመረ (ነገርን፣ ጠብን)።

ጫረታ "***ጨረተ**" ስር "**ጨረታ**"ን ተመ.

ጫቅማ ስ ጉሉ።

ጫተረ ግ ለፋ፣ ደከመ (በስራ)።

ጫት ስ ለጋ ቅጠሉ የሚታኘክና ሱስ የሚያስይዝ የእፅዋት አይነት።

ጫት ቃመ ግ ጫቱን እየቀጠፈና እየቀነጠበ አኘከ።

ጫት ቃሚ ቅ ጫትን አዘውትሮ የሚያኝክ (ሰው)።

ጫነ ግ 1. እቃን፣ ሸቀጥን፣... በመኪና፣ በከብት፣ በመርከብ፣... ላይ አኖረ፣ አደረገ፤ አሸከመ። 2. ከአንድ ሃገር ወደ ሌላ ወሰደ፣ አጓጓዘ (እቃን)። 3.አሳፈረ። *አስር ሰው የጫነ መኪና።* 4. አንዱን በሌላው ላይ ደረበ፣ አኖረ፣ አሳረፈ፣ አስቀመጠ(ከላይ)። *ድንጋይ ጫነበት።*

መጫኛ ስ በከብት ጀርባ ላይ ጭነትን ለማሰር የሚያገለግል ጠፍር።

መጫኛ ነካሽ ስ (የን.አነ.) ሸቀጡን በአህያና በበቅሎ እያጓጓዘ የሚሸጥ ነጋዴ፤ ጠፍር ነካሽም ይባላል።

ጫና ስ 1. ከባድ ሸክም። 2. ከአቅም በላይ የሆነ ስራ ወይም ሃላፊነት። 3. ጭቆና።

ጭነት ስ ሸክም፤ በአጋሰስ፣ በአህያ፣ በመኪና፣... የተጫነ እቃ።

የጭነቱ ልክ ስ አንድ ተሽከርካሪ ሊይዝ የሚችለውና የተፈቀደለት የእቃና የሰው ብዛት ወይም መጠን።

የጭነት መኪና ስ የተለያዩ እቃዎችን የሚሸከም፣ የሚያጓጉዝ (ብዙውን ጊዜ ከባድ መኪና) (ስእሉን መጓጓዣ ስር ተመ.)።

የጭነት ከብት ስ ለጭነት አገልግሎት ማለትም ለሸክም ብቻ የሚውል ከብት፤ አጋሰስ።

ጫን ስ አስር ማድጋ ያህል የሚይዝ የስፍር መለኪያ (አንድ ጫን በቁና ወይም በማድጋ የሚይዘው መጠን እንደየአካባቢው ይለያያል)።

ጫን ጫን ተነፈሰ ግ በጣም ወይም በሃይል ተነፈሰ (ከድካም፣ከበሽታ፣... የተነሳ)።

ጫኝ ስ ሸቀጥን ከቦታ ቦታ በአጋሰስ ወይም በአህያ የሚያጓጉዝ ሰው።

ጫን አለ ግ 1. ተጫነ፣ አጠበቀ። 2. በደለ። 3. ጨቆን አደረገ።

ተጫነ ግ 1. እቃው፣ ሸቀጡ፣... በመኪና፣ በእንስሳ ጀርባ፣ በመርከብ፣... ላይ ተደረገ፣ ለመጓጓዝ ተዘጋጀ ወይም ጉዞ ጀመረ። 2. ነፃነት ነሳ። 3. አጣበቀ፣ ደፈጠጠ፣ ገፋ። 4. ተፅእኖ

ወይም ግፊት አደረገ።

ተጫጫነ ግ ቀፈፈ፥ ከበደ፥ ሰውነት ድክም አለ።

ጫንቃ ስ 1. በትከሻና በትከሻ፥ በአንገትና በጀርባ መካከል ያለው የሰውነት ክፍል፤ ደንደስ። 2. ትከሻ።

በ___ ጫንቃ በ___ ድጋፍ፥ እርዳታ። *በሰው ጫንቃ ይኖራል።*

ጫኖ ስ ከደረቱ በላይ ጥቁር ሆኖ ከጆሮዎቹ አካባቢ ግራጫ መልክ ያለው፥ በሃይቆችና በትናንሽ ወንዞች አካባቢ የሚገኝ፥ በመጠን ከዳክዬ የሚበልጥ የአሞራ አይነት።

ጫኝ "**ጫነ**" ስር ተመ.

ጫካ ስ በብዛት ችፍግ ብሎ የበቀለ ልዩ ልዩ ዛፍ፥ ቁጥቋጦ የሚገኝበት ቦታ፤ ደን።

ጫወታ "***ጨወተ**" ስር "**ጨዋታ**" ን ተመ.

ጫጉላ [ቤት] ስ ሙሽራና ሙሽሪት ለተወሰነ ጊዜ የሚሞሸሩበት ቤት።

ጫጨ(ጫጫ) ግ ኮሰሰ፤ ከሳ፤ ቀጠነ፤ ሰለለ።

ጫጩት ስ 1. ከእንቁላል የወጣ ወይም የተፈለፈለና ገና ያላደገ የዶሮ፥ የወፍ፥ የአሞራ ልጅ። ቅ 2. ትንሽ (ልጅ)።

***ጫጫ**

ጫጫታ ስ ከፍተኛ ድምፅ የሚሰማበት የብዙ ሰው ንግግር፤ ሁካታ።

ተንጫጫ ግ 1. ብዙ ሰው ተሰብስቦ ከፍ ባለ ድምፅ እርስ በርሱ ተነጋገረ፤ አወራ። 2. በብዛት ሆኖ የጩሀት ድምፅ አሰማ (ሰው፥ ወፍ፥ ...)። 3. አለቀሰ (ብዙ ሰው አንድ ላይ)።

አንጫጫ ግ እንዲንጫጫ አደረገ፥ አስጮሀ (ልጆችን፥ ...)።

ጫጫ "**ጫጨ**"ን ተመ

ጫጫረ "**ጫረ**" ስር ተመ.

ጫጫታ "***ጫጫ**" ስር ተመ.

ጫፍ ስ 1. የአንድ ነገር የላይኛው ወይም የታችኛው የመጨረሻው ክፍል። 2. መሃል ያልሆነ፥ ዳር ወይም ጠርዝ። 3. መጨረሻ። *ጉዳዩን ከጫፍ አድርሶታል።* 4. ከዋናው ጉዳይ ወይም አካል ጥቂት ብቻ፥ ትንሽ ነገር፥ ዋናውን ያልሆነ፤ ዝርዝሩን ያልያዘ። *ጫፍ ይዘህ ብዙ አታውራ።*

ጫፌን ንካኝ እስቲ አጠገቤ ደርሰህ ትንሽ ምታኝ የማለትና የማስፈራራት አነጋገር።

ጫፍ ጫፉን በዝርዝር ሳይሆን አንዳንዱን። *የዚህን ወሬ ጫፍ ጫፉን ሰምቼዋለሁ።*

ጬ የ "**ጨ**" ፊደል ሃምስ ዘር።

ጭ የ "**ጨ**" ፊደል ሳድስ ዘር።

ጭለማ "**ጨለመ**" ስር "**ጨለማ**" ን ተመ.

ጭሉፋት "**ጨለፈ**" ስር ተመ.

ጭላሃ ስ ትንሽ እንጎቻ።

ጭላት ስ ጭልፊት።

ጭላዳ ስ ተራራማና ድንጋያማ በሆኑ በኢትዮጵያ ደጋማ ቦታዎች የሚገኝ፥ በጠጉሩ ርዝመትና ለስላሳነት እንዲሁም በቀለሙ ቡናማነት ከሌሎች የዝንጀሮ ዝርያዎች በቀላሉ የሚለይ፥ ከመቀመጫው በተጨማሪ በደረቱና በአንገቱ ላይ መላጣ ያለው የዝንጀሮ አይነት (ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።

ጭላጭ "**ጨለጠ**" ስር ተመ.

ጭል

ጭላንጭል ስ 1. የማድግዳ፥ የመስኮት፥ የጣራ፥... ቀዳዳ (ብርሃን ዘልቆ የሚገባበት)። 2. መጠነኛ እይታ (የነገር፥ የተስፋ)። *የተስፋ ጭላንጭል።*

ጭልታ ስ የነገር፥ የሃሳብ ጭላንጭል።

ጭል ጭል አለ ግ 1. በትንሽ በትንሹ ታየ(መብራት)። *ኩራዟ ጭል ጭል ትላለች።* 2. በጥቂት በጥቂቱ ወረደ፥ ፈሰሰ(ውሃ)።

ጭልል

ጭልል አለ (ጭል አለ) ግ አንዳች አልባ ሆነ፥ ጭር አለ።

ጭል [ል] ያለ ሜዳ ለጥ ያለ ሜዳ።

ጭልቃ "***ጨለቀ**" ስር ተመ.

ጭልታ "**ጭል**" ስር ተመ.

ጭልጌ(ጭልጊ) ስ ከወይፈን ቆዳ የሚዘጋጅ ስለቻ።

ጭልፊት ስ 1. በክረምት የማትታይ (ጫጩት፥ ሲጋ፥... የምትነጥቅ) የአሞራ አይነት (ስእሉን አሞራ ስር ተመ.)። 2.(ዘይ.) ነጣቂ ሌባ፥ ሞጭላፋ።

ጭልፋ "**ጨለፈ**" ስር ተመ.

ጭማሪ "**ጨመረ**" ስር ተመ.

ጭማቂ "**ጨመቀ**" ስር ተመ.

ጭም አለ ግ ፀጥ፥ ጭጭ አለ።

ጭምር "**ጨመረ**" ስር ተመ.

ጭምብል ስ ከሹራብ ወይም ከጨርቅ ወይም ከእንጨት፥... በተለያየ ቅርፅ የሚሰራና አንድ ሰው ማንነቱ በተመልካች ተለይቶ እንዳይታወቅ ፊቱን የሚደብቅበት ወይም የሚከልልበት የፊት ገፅታ ሽፋን ወይም መሸፈኛ።

ጭምት "**ጨመተ**" ስር ተመ.

ጭምጭማት "**ጨመጨመ**" ስር ተመ.

ጭምጭምታ ስ በይፋ ያልወጣ ወይም

ያልተረጋገጠ ወሬ።

ጭረት፡“ጫረ” ስር ተመ.

ጭሩ ስ ላባዎቹ ጥቁር ሆነው ሊላው አካሉ አሸዋማ መልክ ያለው ድንቢጥን የሚያክል የወፍ ዘር (ስእሉን ወፍ ስር ተመ.)።

ጭሪ ስ የከብቶችን ቆዳ በምንቃሯ እየወጋች የምታቆስልና ደም የምትመጥ አፈቀይ የወፍ አይነት፣ እረኛ (ስእሉን ወፍ ስር ተመ.)።

ጭራ ስ 1. ጅራት። 2. የአንድ ነገር የኋለኛ አካል ክፍል። 3. ከፈረስ ወይም ከበሬ ጅራት ወይም ከቃጫ፣... የሚሰራ የዝንብ መከላከያ። 4. ተከታይ፣ ከኋላ ከኋላ ሱክ ሱክ የሚል። 5. በአስተሳሰብ፣ በውድድር፣... ወደኋላ የቀረ። 6. የአንድ ነገር ፍንጭ፣ ምልክት።

ጭራ 3ኛ ፍቺ

ጭራ ቆናኝ የዝንብ መከላከያ ጭራ እየጎነጎነና እያስጌጠ የሚሰራ ባለሙያ።

ጭራ አወጣ/ አበቀለ በጣም ተናደደ።

ጭራው አይያዝም አንድ ቦታ ላይ አይቀመጥም፣ ሲፈለግ አይገኝም (ሰው)።

ጭራውን ቆላ 1. ጭራውን አወዛወዘ፣ ነስነሰ (ፈረስ፣ ውሻ፣...)። 2. ተፍነከነከ፣ በጣም ተደሰተ። 3. ተለማመጠ።

ጭራውን ይዞ ተከራከረ የገዛውን ከብት ለእኔ ነው ባይ ሳይለቅ ወይም ሳይሰጥ በእጁ እንዳደረገ ተከራከረ።

ጭራው ጮሌ በጣም ብልጥ የሆነ፣ ቀልጣፋ።

ጭራሮ ስ 1. ለማገዶ የሚያገለግል የደረቀ ቀጫጭን እንጨት ወይም የዛፍ ቅርንጫፍ። ቅ 2. ቀጭን (እግር)።

ጭራሽ “ጨረሰ” ስር ተመ.

ጭራቅ ስ 1. አራት አይና ነው ተብሎ የሚታሰብና ሰው ይበላል የሚባል የሰው ጅብ። ቅ 2. አረመኔ፣ ጨካኝ፣ ርህራሄ የሌለው።

ጭራንፎ ስ የዛፍ ቅርንጫፍ፣ ዛፍ ላይ እንዳለ የደረቀ ጭራሮ።

ጭሬ ስ ረዥም ጦር።

ጭር

ጭር አለ ግ 1. ፀጥ፣ ረጭ አለ፣ ድምፅ ጠፋ። 2. በአካባቢው የሚንቀሳቀስ ሰው ጠፋ፣ ባዶ ሆነ። 3. ሰውነቱ በድንጋጤ፣ በህመም፣... የተነሳ ኮሳ፣ ኮሰሰ። 4. የመጥረጊያ ደወል የሚያሰማውን አይነት ድምፅ አሰማ።

ጭር አለች እንቁላል መጣል ተወች (ዶሮ)።

ጭርቂያም “*ጨረቀ” ስር ተመ.

ጭርት ስ በሰው አካል ላይ (ብዙውን ጊዜ አንገትና ፊት ላይ) የሚታይና እያሳከከ ስፋት የሚጨምር የቆዳ በሽታ።

ጭርንቁስ ስ ቡትቶ፣ የተጣጣፈ አሮጌ ጨርቅ፣

ጭርንቁሳም ቅ (ስድብ) ቡትቶ ለባሽ።

ጭቁን “ጨቆነ” ስር ተመ.

ጭቁኝ ስ መድሃኒትነት አለው የሚባልና ሽታው የማያስደስት (የሚያንገሸግሽ) የቅጠል አይነት።

ጭቃ “ጨቀየ” ስር ተመ.

ጭቅቅት ስ የሰውነት ቆሻሻ፣ እድፍ።

ጭቅቅታም ቅ (ስድብ) እድፋም፣ ቆሻሻ።

ጭቅና ስ፣ ከሽንጥ ጋር አብሮ የሚወጣና በጣም ለስላሳ የሆነ የብልት አይነት።

ጭቅጭቀኛ “ጨቀጨቀ^{1} ” ስር ተመ.

ጭቅጭቅ ዝ.ከ.

ጭቆና “ጨቆነ” ስር ተመ.

ጭባ ቅ (ስድብ) አጭርና ቀጭን የሆነ፣ ድውይ።

ጭብጥ “ጨበጠ” ስር ተመ.

ጭብጥ ዝ.ከ.

ጭብጦ ዝ.ከ.

ጭብጨባ “*ጨበጨበ” ስር ተመ.

ጭቦ ስ ግፍ፣ በደል፣ በሸር፣ በተንኮል፣ በሃሰት የተፈፀመ ነገር።

ጭቦኛ ቅ ግፈኛ፣ በደለኛ፣ በተንኮል፣ በሃሰት የሚሰራ።

ጭነት “ጫነ” ስር ተመ.

ጭን ስ ከጉልበት በላይ ከብሽሽት በታች ያለ የሰውነት ክፍል (ስእሉን ሰውነት ስር ተመ.)።

የጭን በቅሎ ስ ባለቤቷ ብቻ የሚቀመጥባት በቅሎ።

የጭን ገረድ ስ በጥንት ዘመን በዘመቻ ጊዜ ከጌታዋ ጋር አብራ የምትሄድና የምትተኛ ሴት።

የጭን ፈረስ ስ ባለቤቱ ብቻ የሚቀመጠው ወይም የሚጋልበው ፈረስ።

ጭንቀታም “ጨነቀ” ስር ተመ.

ጭንቀት ዝ.ከ.

ጭንቁላ ስ ማሰሮ።

ጭንቁር^{1} ስ በፊት ላይ (ብዙውን ጊዜም አፍንጫ ላይ) የሚወጣና አፍንጫን የሚያበላሽ ቁስል፣ ቫይኝ፣ ቁንጭር።

ጭንቁር^{2} “ጨንቆረ” ስር ተመ.

ጭንቁርቁር ዝ.ከ.

ጭንቅ "ጨነቀ" ስር ተመ.

ጭንቅላት ስ 1 የራስ ቅል። 2 አውቀት፣ ማስተዋል፣ የማመዛዘን ችሎታ።

ጭንቅላቱ ላሸቀል አውቀቱ ወይም የማመዛዘን፣ የማስተዋል ችሎታው ቀድሞ ከነበረበት ደረጃ ቀንሷል።

ጭንቅላት የለውም አያመዛዝንም።

ጭንቅላተ ቢስ (ስድብ) ማመዛዘን የማይችል።

ጭንቅላታም ቅ (ስድብ) ትልቅ ጭንቅላት ያለው።

ጭንቅሉ ዝ.ከ.

ጭንብስብስ "ጨነበሰ" ስር ተመ

ጭንጋፍ "ጨነገፈ" ስር ተመ.

ጭንጩ ቅ ዘሩ ከሌላ ጋር ያልተደባለቀ ወይም ያልተዋሃደ። *ጭንጩ ላማራ።*

ጭንጫ ስ 1. ድንጋያማ ወይም አለታማ መሬት። 2. በቀላሉ የማይገሰስ (የማይደፈር) የልጃገረድ ድንግልና።

ጭካኔ "ጨከነ" ስር ተመ.

ጭኮ ስ ከበሶ ዱቄት በቅቤ ታሽቶ የሚዘጋጅ ምግብ።

ጭው

ጭው አለ ግ 1. በጆሮ ውስጥ የጩኸት ድምፅ ተሰማ። 2. ከሳ፣ ገረጣ (የሰው ፊት)።

ጭው ያለ ሜዳ አቀበትና ቁልቁለት የሌለው ሰጥ ያለ ሜዳ።

ጭው ያለ በረሃ ምንም ሰው የሌለበትና ድምፅ የማይሰማበት በረሃ።

ጭው ጭው አለ ጮሀ፤የጫጩት አይነት ድምፅ አሰማ።

ጭውውት "*ጨወተ" ስር ተመ.

ጭዳ ስ ለአምልኮ ባእድ የሚደረግ እርድ።

ጭዳ አለ ግ 1. ለአምልኮ ባእድ መስዋእት አቀረበ ወይም ደም አፈሰሰ። 2. ገደለ። *ተጠንቀቅ ጭዳ እንዳልልህ።*

ጭድ ስ የጤፍ ገለባ።

ጭገራም "ጨጎረ" ስር ተመ.

ጭገሬታ "ጨገሬታ" ን ተመ.

ጭገር "ጨጎረ" ስር ተመ.

ጭጉኝ ስ ጭገር።

ጭጋግ "ጨገገ" ስር ተመ.

ጭጎት ስ በገጠር አካባቢ በጭቃ ወይም በግንብ ቤት ግድግዳ ላይ የሚሰራ የኩራዝና የአንዳንድ እቃ ማስቀመጫ ቦታ።

ጭጎጎት ስ ፍሬው ልብስ ላይ የሚከስከስና የሚጣበቅ የእፅዋት አይነት።

ጭጎጎት ፊት የማይጠዳው፣ ፊቱ የማይፈታ።

ጭጫን ስ ቁጫጭ።

ጭጭ

ጭጭ አለ ግ 1. ፀጥ፣ ረጭ፣ ዝም አለ፤ ሳይናገር ቀረ። 2. በድንገት ሞተ።

ጭጭ እንዳትል ድምፅ እንዳታሰማ ወይም እንዳትናገር።

ጭጭ ምጭጭ የለም ድምፅ ማሰማት ወይም መተንፈስ የለም።

ጭፈራ "ጨፈረ" ስር ተመ.

ጭፋር ስ 1 የቅንድብ ፀጉር። 2. የዘንባባ፣ የቴምር ወይም የሰሌን ቅጠል።

ጭፋሮ "ጨፈረ" ስር ተመ.

ጭፍልቅ "ጨፈለቀ" ስር ተመ.

ጭፍን "ጨፈነ" ስር ተመ.

ጭፍንፍን ዝ.ከ.

ጭፍግግ "ጨፈገገ" ስር ተመ.

ጭፍጨፋ "ጨፈጨፈ" ስር ተመ.

ጭፍጫሬ ዝ.ከ.

ጮ የ"ጨ" ፊደል ሳብእ ዘር።

ጮሀ ግ 1. ከፍ ያለ ድምፅ አሰማ ወይም ሰጠ። 2. ኡኡ፣ እሪ፣... አለ፣ የድረሱልኝ ጥሪ አሰማ። 3. ድምፅ አሰማ(ዶሮ፣ ውሻ፣ ጅብ፣...)። 4. አቤት አለ፤ አቤቱታ አቀረበ(ለዳኛ፣ ለሹም)። 5. ድምፅ አውጥቶ አለቀሰ። 6. ተቆጣ።

ጮሀበት ተቆጣው።

ጯሂ ቅ 1. ድምፁን ከፍ አድርጎ የሚናገር፣ ለፍላፊ። 2. (የጥንት አነጋገር) አቤቱታ አቅራቢ።

ጩሀት ስ 1. ከሰው፣ ከእንስሳ ወይም ከሌላ ነገር የሚወጣ ከፍተኛ ድምፅ። 2. ጫጫታ፣ ሁካታ።3. እሪታ፣ኡኡታ።

ጩሀቴን ቀሙኝ አቤቱታ ማቅረብ ወይም ብሶቱን ማሰማት፣ መክሰስ... የሚገባው ተበዳዩ እያለ፤ በደል አድራጊው (ፈፃሚው) በደል እንደደረሰበት ሆኖ ተናገረ፤ በተበዳዩ ወገን ላይ እሮሮ አሰማ ለማለት የሚነገር አባባል።

ጮክ አለ ግ ድምፁን ከፍ አድርጎ ተናገረ።

ተጮሀ ግ ኡኡ፣ እሪ፣... ተባለ፤ ተለቀሰ፤ ኡኡታ ተሰማ (በሃዘን፣ በድንጋጤ፣ እርዳታን በመሻት)።

ተጯጯሀ ግ 1. ሳይደማመጥ ሁሉም በየፊናው ተናገረ፤ ተንጫጫ። 2. ተሳቀሰ።

አጮሀ ግ 1. ከፍ ያለ ድምፅ እንዲያሰማ አደረገ። 2. መታ። *በጥፊ አጮሀው።*

አጯጯሀ ግ ሽብር በመፍጠር እንዲጮህ አደረገ፤ አንጫጫ።

አስጮሀ ግ እንዲጮህ ወይም ጩሀት እንዲያሰማ አደረገ።

***ጮለ**

አጮለ ግ በጥፊ መታ፤ አጠናገረ።

ጮሌ ቅ ብልጥ።

ጮመ ግ በጣም ሰባ።

ጮማ ስ በጣም ሰባ ወይም ነጭ የሆነ የከብት ስጋ።

ጮረረ ግ ወረደ፤ ተንቆረቆረ፤ ፈሰሰ (ፈሳሽ)።

መንጮረር ስ ጣሪያ ላይ የሚሰራ የዝናብ ውሃ መውረጃ አሸንዳ።

ጮራ "*ጮረረ²" ስር ተመ.

ጮርቃ "**ጨረቀ**" ስር ተመ.

ጮቄ ስ በጣም ደጋ የሆነና ጨቀጨቅ ያለበት ቦታ።

ጮቅ¹ ስ የክረምት ጭቃ።

ጮቅ² ስ በእግር ጣቶች መሃል የሚወጣ ቁስል ወይም ስንጥቃት።

ጮቤ ስ ሁለት እግርን በአንድነት እያነሱ የራስን ቂጥ በመምታት የሚደረግ ዝላይ።

ጮቤ መታ/ ረገጠ በጣም ተደሰተ።

ጮካ ቅ ጮሌ፤ ብልጥ።

ጮጮ¹ ስ ከስንደዶ፤ ከአክርማ ወይም ከግራምጣ ተሰፍቶ ለወተት ማለቢያነት የሚያገለግል የቤት እቃ (ስእሉን የስፌት እቃ ስር ተመ.)።

ጮጮ² "**ጠጮ**"ን ተመ.

ጯ የ "**ጨ**" ፊደል ፍንፅቅ ዘር።

ጯሂ "**ጮሀ**" ስር ተመ.

ጸ

ጸ ከ"ጨ" ፊደል ዘር ቀጥሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል (ግእዙ ሆሄ)።

ጹ የ"ጸ" ፊደል ካዕብ ዘር።

ጺ የ"ጸ" ፊደል ሣልስ ዘር።

ጻ የ "ጸ"ፊደል ራብእ ዘር።

ጻጉሜን (ጻጉሜ፥ ጻጉሚት) ስ በዘመነ ዮሃንስ፥ ማቴዎስና ማርቆስ አምስት አምስት ቀናት በዘመነ ሉቃስ ግን ስድስት ቀናት ያሉትና ከነሃሴ ቀጥሎ የሚመጣ የአመቱ አስራ ሶስተኛ ወር።

ጻጻስ (ብ.ቁ. **ጻጻሳት**) ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ማእረግ ከኤጲስቆጶስ በላይ ከሊቀጻጻስ በታች የሆነ መንፈሳዊ ሹመት።

ጽጽስና ስ የጽጽስና ማእረግ ወይም ስልጣን።

አጻጻሰ ን የጽጽስና ማእረግ ወይም ስልጣን ሰጠ።

ጼ የ"ጸ"ፊደል ሃምስ ዘር።

ጽ የ"ጸ" ፊደል ሳድስ ዘር።

ጾ የ"ጸ" ፊደል ሳብእ ዘር።

ፀ

ፀ ከ"ጸ" ፊደል ዘር ቀጥሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል (ግእዙ ሆሄ) ፡፡

ፀሃይ ስ 1. መሬትና ሌሎች ፕላኔቶች ዙሪያዋን የሚዞሩዋት፥ ብርሃንና ሙቀት የምትሰጥ ኮከብ፤ ጀምበር፡፡ 2. ከፀሃይ የሚገኝ ሙቀት፡፡

ፀሃይ መታው /ከካው 1. (ለሰው) የፀሃይ ሙቀት ጎዳው፥ አደከመው፡፡ 2. ፀሃይ አደረቀው፥ ሞቀው፡፡

ፀሃይ ወጣ 1. የፀሃይ ብርሃን ታየ፥ ነጋ፥ ቀን ሆነ፡፡ 2. (ዘይ.) ችግር፥ ሃዘን፥... ተወገደ፥ ደስታ ሆነ፡፡

ፀሃይ ገባች /ጠለቀች ጨለመ፥ መሸ፡፡

የፀሃይ ቆብ ስ ለፀሃይና ለብርድ መከላከያ ሲባል የሚደረግ ቆብ፡፡

የፀሃይ ግርዶሽ ስ የፀሃይ ብርሃን በከፊል ወይም በሙሉ በጨረቃ መከለል ወይም መጋረድ፡፡

ፀሃፊ "ፃፈ" ስር ተመ.

ፀለየ ግ አምላክን ለመነ፥ ተማፀነ፥ ወይም አመሰገነ፡፡

ፀሎት ስ ለአምላክ የሚቀርብ ልመና፥ምስጋና፡፡

ፀሎት አደረሰ ፀሎት ፀለየ፥ ደገመ፡፡

ፀሎተ ሃሙስ ስ ከፋሲካ እሁድ በፊት የሚገኘው ሃሙስ የሚጠራበት ስም፡፡

ፀሎተ ማእድ ስ ከማእድ በፊትና በኋላ የሚፀለይ ፀሎት፡፡

ፀሎተ በረድ ስ በረዶ እንዳይጥልና በሰብል ላይ ጉዳት እንዳያደርስ የሚፀለይ ፀሎት፡፡

ፀሎተኛ ቅ ለፈጣሪው ዘወትር ፀሎት የሚያቀርብ፤ ሃይማኖተኛ፡፡

*ፀረረ

ፀር(ጠር) ስ ጠላት ወይም ተስማሚ ያልሆነ ወይም ተቃራኒ ነገር፡፡

ፀረ ___ የ ___ ጠላት ወይም ፀር ለማለት የሚያገለግል ክፍለ ቃል፡፡ *ፀረ ዲሞክራሲ /ፀረ ኣይሮፕላን* ፡፡

ተፃረረ ግ ተቃወመ፥ተቃረነ፥ ተጣላ፡፡

ተፃራሪ ቅ ተቃዋሚ፥ ተቃራኒ፥ ባላንጣ፡፡

ፀበል(ጠበል) ስ 1. ህመምተኞች ፈውስ ለማግኘት የሚጠጡት ወይም የሚጠመቁበት የተፀለየበት ውሃ፡፡ 2. በተፈጥሮ ፈዋሽነት ያለውና ብዙውን ጊዜ በታቦት ስም የሚጠራ የምንጭ ውሃ፡፡ 3. ለክርስትና፥ ለዝክር፥ ለማህበር፥ ለተዝካር የተዘጋጀ ድግስ (ምግብ፥ መጠጥ)፡፡

ፀበል ቅመስ (ለክርስትና፥ ለዝክር፥... የተዘጋጀውን) መጥተህ ተጋበዝ፡፡

ፀበል ፀዲቅ (ጠበል ጠዲቅ) ስ ለክርስትና፥ ለዝክር፥... የተዘጋጀ ድግስ (ምግብና መጠጥ)፡፡

ፀበለተኛ (ጠበለተኛ) ስ በህመም ምክንያት ፀበል በመጠጣትና በመጠመቅ ላይ ያለ ሰው፡፡

*ፀበረቀ

ነፀብራቅ ስ 1. ብልጭታ፡፡ 2. አንድን ሁኔታ፥ አስተሳሰብ የሚያመለክት ድርጊት ወይም ሃሳብ፡፡

ተንፀባረቀ ግ 1. ብርሃን እንደመስታወትና ውሃ ባሉ አካላት ላይ ካረፈ በኋላ ተቀልብሶ በሌላ አካል ላይ ብልጭልጭታ አሳየ፡፡ 2 ተብለጨለጨ፡፡ 3. የራስ የሆነ ወይም ከሌላ ሰው የተወሰደ አንድ አይነት አስተሳሰብ በንግግር ወይም በድርጊት ላይ ታየ፥ ተከሰተ፥ ተገለጠ፡፡

አንፀባረቀ ግ 1. አብረቀረቀ፥አብለጨለጨ፡፡ 2. አማረ፥ ተዋበ፡፡ 3. የራስ ወይም የሌላ ሰው የሆነን አንድ አስተሳሰብ በንግግር ወይም በድርጊት አሳየ፥ አስተጋባ፥ ግልፅ አደረገ፡፡

አንፀባራቂ ቅ 1. የሚያብለጨልጭ፡፡ 2. የሚያምር፥ ውብ፡፡

ፀነሰ ግ ወጠነ፡፡

ፀነሰች ግ በማህፀኗ ሽል ያዘች፥ አረገዘች፡፡

ፅንስ ስ 1.ሽል፡፡ 2. ውጥን፡፡

ፅንሱ ወረደ ጨነገፈ፡፡

ፅንሰ ሃሳብ ስ ስለአንድ ነገር በአእምሮ ውስጥ የተቀረፀ ግንዛቤ፡፡

ተፀነሰ ግ 1. ተረገዘ፡፡2.ተወጠነ፡፡

ፀና ግ 1. ረጋ፥ ቆመ፡፡ 2. ፀደቀ(ፍርድ፥ ውሳኔ)፡፡

ፅናት(ጥናት) ስ ያለማወላወል፥ በአንድ አቋም ላይ መርጋት፡፡

ፀናፅል ስ መዘምራን (ካህናት) ማህሌት በሚቆሙበት ጊዜ በቀኝ እጃቸው ይዘው ወደላይና ወደታች በማንቀሳቀስ የሚያቅጨለጭሉት የቤተክርስቲያን የዝማሬ መሳሪያ (ስእሉን የሙዚቃ መሳሪያ ስር ተመ.)፡፡

ፀኣዳ ስ 1. ንፁህ፥ የፀዳ፡፡ 2. ነጭ፡፡

*ፀየፈ

ፀያፍ (ጠያፍ) ቅ 1. ነውር፥ የሚያስጠላ፥ የሚያስቀይም፡፡ 2.ሰው ፊት ወይም በአደባባይ መነገር የማይገባው (ነገር)፡፡

ፅዩፍ(ጥዩፍ) ቅ ተጠያፊ፥ እጅግ ጥንቁቅ (የማይፈልገውን ነገር ወይም ምግብ ባለመንካት ወይም ባለመጠቀም)፡፡

ተፀየፈ(ተጠየፈ) ግ ናቀ፥ ጠላ፡፡

ተፀያፊ ቅ ንቀትን፥ ጥላቻን የሚያሳይ።

አስፀየፈ ግ አስጠላ፥ አስከፋ፥ አስቀየመ።

አስፀያፊ ቅ 1. የሚያስጠላ፥ የሚያስቀይም። 2. መጥፎ፥ ነውር፥ አሳፋሪ የሆነ።

ፀደቀ¹ ግ 1. መንግስተ ሰማያት ወይም ገነት ገባ። 2 ተመቸው፥ የሚስማማውን አገኘ።

ፀደቀበት የሚፈልገውን በመስጠት ወይም በማድረግ ችግሩን አቃለለለት።

ፀዲቅ (ፃዲቅ፥ጣዲቅ) ስ በመላእክት፥ በፃድቃን፥... ስም ወይም ሟችን ለመዘከር የሚጋገር ዳቦ።

ፃድቅ (ብ. ቁ. **ፃድቃን**) ቅ 1. ለነፍሱ ያደረ ሃይማኖተኛ ሰው። 2. መልካም፥ ደግ ሰው። 3. በመንፈሳዊ ተግባሩ ከቅዱስነት ደረጃ የደረሰ መሆኑ ታምኖበት በስሙ ቤተክርስቲያን የተሰራለትና ፅላት የተቀረፀለት፥ የበቃ ሰው።

ፅድቅ ስ 1. መልካም ስራ ለሰራና የእግዚአብሄርን ትእዛዝ ለፈፀመ ከእግዚአብሄር የሚሰጥ ሰማያዊ ዋጋ። 2. መልካም፥ በጎ ስራ።

ፀደቀ² 1. የተተከለ ችግኝ ለመደ፥ ለመለመ፥ ስር ሰደደ። 2. ጠና፥ ተቀባይነት አገኘ፥ ይሁን ተባለ (ሃሳብ፥ውሳኔ፥ ...)።

ፀደይ ስ ከመጋቢት 26 እስከ ሰኔ 25 ያለው ጊዜ፥ የበልግ ወቅት፥ የዘር ወራት።

ፀዲቅ "ፀደቀ" ስር ተመ.

ፀዳ (ጠዳ) ግ ነፃ፥ ጠራ፥ ንፁህ ሆነ። *ቤቱ ፀዳ መስሪያ ቤቱ ከሌቦች ፀዳ።*

ፅዱ ቅ ንፁህ፥ ያማረ፥ የፀዳ።

ፅዳት ስ ንፅህና።

የፅዳት ሰራተኛ ስ ቤትን ወይም ቢሮን፥... በማፅዳት የሚተዳደር ሰው።

ተፀዳዳ ግ ሽንትን ወይም አይነ ምድርን ከሰውነቱ ውስጥ አስወገደ ወይም አስወጣ።

መፀዳጃ [ቤት] ስ ሽንት ቤት።

አፀዳ ግ 1. አጠበ፥ ንፁህ አደረገ። 2. ወለወለ፥ ጠረገ። 3. አጠራ፥ ንፁህ አደረገ (ከሌባ፥ ከወንበዴ፥...)።

አይፀዳሽ ቅ ደስተኛ ያልሆነ፥ ብዙ ጊዜ ፊቱ ላይ ደስታ የማይታይበት።

ፀዳል ስ ብርሃን ወይም የብርሃን ፍንጣቂ።

ፀጉር (ጠጉር) ስ 1. በእንስሳት አካል ላይ የሚበቅል ጭገር። 2. በሰው ገላ በተለይም በጭንቅላት ላይ ብዛት ያለው ሆኖ የሚበቅል ጭገር።3. እንደ ሹራብ ባሉ ልብሶች ላይ የሚገኝ እንደፀጉር ያለ የሚነጭ ጭገር።

ጉሩ ሸሸ ፀጉሩ መመለጥ ጀመረ።

ፀጉር ሰንጠቃ በአንድ ጉዳይ ላይ ከሚያስፈልገው በላይ ጥቃቅን የሆኑ ነጥቦችን ማንሳት።

ፀጉረ ሉጫ ለስላሳ ፀጉር ያለው ሰው።

ፀጉረ ልውጥ ለአካባቢው እንግዳ የሆነ አዲስ ሰው።

ፀጉር ቆራጭ /አስተካካይ ስ የወንዶችን ፀጉር የሚቆርጥ፥ የሚያስተካክልና የሚያሳምር ባለሙያ።

ፀጉር ሰሪ ስ የሴቶችን ፀጉር በመቁረጥ፥ በመተኮስ፥በመጎንጎን፥ ... የሚያሳምር ባለሙያ።

[የ] ፀጉር አሰራር ስ የተለያዩ አይነቶች የፀጉር አጎናጎን፥ አሰሟሟት፥... መንገዶች (ብዙውን ጊዜ የሴቶች)።



[የ] ፀጉር አሰራር

ፀጋ ስ አምላካዊ ስጦታ፥ ሃብት፥ ረድኤት።

ፀጥ

ፀጥታ ስ 1. ዝምታ ወይም የድምፅ አለመኖር። 2. እርጋታ፥ ሰላም።

ፀጥታ ነሳ ሰላም ነሳ፥ አወከ፥ ረበሸ።

ፀጥታ አስከባሪ ስ ሁከትን ወይም ረብሻን የሚቆጣጠርና የሚከላከል ሰላም አስጠባቂ ወታደራዊ ሃይል።

የፀጥታ ምክር ቤት ስ ላምስት ቋሚ የሆኑና በየጊዜው የሚቀየሩ አስር አባል ሃገሮች ያሉት፥ የአለምን ሰላም ለመጠበቅ በተባበሩት መንግስታት ስር የተቋቋመ ድርጅት።

ፀጥተኛ ቅ 1. ዝምተኛ፥ ጨዋ። 2. ጫጫታ ወይም ሁካታ የሌለበት ሰላማዊ (ቦታ)።

ፀጥ አለ ግ 1. ዝም ወይም ጭጭ አለ። 2. ሰላም ሰፈነ። *አገሩ ፀጥ ብሏል።* 3. (ዘይ.) አረፈ፥ ሞተ።

ፀጥ አሰኘ ግ ዝም ወይም ጭጭ እንዲል አደረገ።

ፀጥ አደረገ ግ 1. ዝ.ከ. ። 2. ገደለ።

ፀፀተ ግ ባላደረግሁ ወይም ባልሰራሁ አሰኘ፥ቆጨ።

ፀፀት ስ ባላደረግሁ፡ ባልሰራሁ፡ ባልተናገርሁ፡… የሚያሰኝ የሃዘን ወይም የቁጭት ስሜት።

ተፀፀተ ግ ባላደረግሁ፥ ባልሰራሁ፥… አለ፥ ተቆጨ፥ ባደረገው፡ በሰራው፡… አዘነ፥ ቅር ተሰኘ።

ፁ የ"ፀ"ፊደል ካእብ ዘር።

ፂ የ"ፀ" ፊደል ሳልስ ዘር።

ፂም (ጢም) ስ በአገጭ፡ በጉንጩና በከንፈር አካባቢ የሚበቅል ፀጉር።

ፂም አወጣ ጺም አበቀለ።

ፂም መላጫ ስ ምላጭን በውስጡ መያዝ የሚችልና ለመላጫነት የሚያገለግል ባለእጀታ መሳሪያ።

ፃ የ"ፀ" ፊደል ራብእ ዘር።

ፃህል ስ የቅዱስ ቁርባን መያዣና ማቅረቢያ ዝርግ ሳህን።

ፃእረሞት "ጣእረ ሞት"ን ተመ.

ፃእር "ጣእር"ን ተመ.

ፃዲቅ "ፀደቀ" ስር ተመ.

ፃድቅ ዝ.ከ.

ፃፈ ግ 1. በወረቀት፡ በብራና፡… ላይ ቀለም ባለው ነገር (ብእር፥ እስክሪብቶ፥…) የፊደላትን ቅርፅ አስቀመጠ፤ ከተበ። 2. ፅሁፍ ወይም ድርሰት አዘጋጀ፤ ደረሰ። 3. በፅሁፍ ገለፀ ወይም አሳወቀ። 4. ደብዳቤ ላከ። 5. ቀለም በማውረድ በወረቀት ወይም በብራና ላይ ምልክት ማድረግ ቻለ (ብእር፥ እስክሪብቶ)። *እስክሪብቶው መፃፍ ጀመረ።*

መጣጥፍ ስ በአንድ ርእስ ላይ የተፃፈን ማብራሪያ፥ ገለፃ፡ ምርምር፡… የያዘ አጭር ፅሁፍ።

መፅሃፍ (ብ.ቁ .መፃህፍት) ስ በእጅ ወይም በታይፕ ወይም በህትመት መሳሪያ የተፃፈ፡ ብዙ ገፆች ያሉትና በጥራዝ መልክ የተዘጋጀ ፅሁፍ።

መፅሃፍ ገላጭ ኮከብ ቆጣሪ፥ ጠንቋይ።

መፅሃፍ ቅዱስ ስ ብሉይና ሃዲስ ኪዳንን አጣምሮ የያዘ መፅሃፍ።

ፀሃፊ ስ 1. በፅሁፍ ስራ ላይ የተሰማራ ሰራተኛ። 2. ለአንድ ባለስልጣን ደብዳቤዎችን የማርቀቅና በታይፕ የመፃፍ፡ መዝገብን የመያዝ፥ መልእክቶችን የመቀበል፥.. ስራ የሚያከናውን ሰራተኛ። 3. ፅሁፍ አዘጋጅ ወይም ደራሲ።

ፀሃፊ ትእዛዝ ስ ከንጉስ የሚሰጡ ትእዛዞችን የሚፅፍና የሚልክ እንዲሁም ከውጭ የሚመጡ ደብዳቤዎችን እየተቀበለ ለንጉስ የሚያቀርብ የሚኒስትርነት ማእረግ የነበረው ባለስልጣን።

ፅሁፍ ስ 1. በወረቀት፥ በብራና፥… ላይ የተፃፈ ወይም የሰፈረ ነገር። 2. በአንድ ርእስ ጉዳይ ላይ የተጠናቀረ ዘገባ። 3. የአፃፃፍ ወይም የፊደል አጣጣል ሁኔታ።

የፅሁፍ ፈተና ስ ለቀረበ ጥያቄ መልሱ በፅሁፍ ብቻ የሚቀርብበት ወይም የሚሰጥበት የፈተና አይነት።

ፅህፈት ስ 1. በቀለም፥ በብእር፥… አማካኝነት ወረቀት፡ ብራና፡… ላይ የሰፈረ ነገር። 2. አፃፃፍ፥ የፊደል አጣጣል። 3. ለተለያየ ነገር መድሃኒት ወይም መፍትሄ ይሆናል እየተባለ በተለያየ ቀለም በወረቀት፡ በብራና፥… ላይ ተፅፎና ተጠቅልሎ በሰውነት ላይ የሚታሰር ክታብ።

የፅህፈት መሳሪያ ስ እንደ እርሳስ፡ እስክሪብቶ፥ ወረቀት፡ ማስመሪያ፡.. የመሳሰሉና ለፅሁፍ ስራ የሚያገለግሉ እቃዎች።

የፅህፈት ስራ ስ ከፅሁፍ ስራ ጋር የተያያዘ ስራ።

የፅህፈት ጠረጴዛ ስ የፅህፈት ስራ የሚከናወንበት ጠረጴዛ።

ፅህፈት ቤት ስ የአንድ ድርጅት ወይም መስሪያ ቤት የአስተዳደር፥ የፅህፈት ስራ፥… የሚከናወንበት ቦታ፥ ቢሮ።

ተፃፃፈ ግ መልእክትን በፅሁፍ ተለዋወጠ።

ፄ የ"ፀ" ፊደል ሃምስ ዘር።

ፅ የ"ፀ" ፊደል ሳድስ ዘር።

ፅሁፍ "ፃፈ" ስር ተመ.

ፅህፈት ዝ.ከ.

ፅላት ስ ታቦት፤ በላዩ ላይ ስመ እግዚአብሄር የተፃፈበት የእንጨት ሰሌዳ።

ፅላተ ሙሴ /እሬት/ ኪዳን ስ በብሉይ ኪዳን እንደተፃፈው እግዚአብሄር ለሙሴ የሰጠውና አስርቱ ትእዛዛት የተፃፉበት የድንጋይ ሰሌዳ።

ፅልመት ስ 1. ጨለማ። 2. ጥቁረት።

ፅልማሞት (ጥልማሞት) ስ 1. ጥቅጥቅ ያለ ጨለማ። 2. በጣም የጠቆረ፥ ጥቁርሻ የመሰለ ነገር።

ፅልምያኮስ (ጥልም ያኮስ) ቅ 1. በጣም ጥቁር የሆነ፥ ጠቋራ። ስ 2. ሰይጣን።

ፅሞና (ጥሞና) ስ እርጋታ፥ ዝግታ።

በፅሞና በእርጋታ። *የተነገረውን ሁሉ በፅሞና አዳመጠ።*

ፅኑ "ጠና" ስር ተመ.

ፅና "ፅንሃህ"ን ተመ.

ፅናት^{1} "ፀና" ስር ተመ.

ፅናት^{2} "ጠና" ስር ተመ.

ፅንሃህ (ፅንሃ፥ ፅና፥ ጥና) ስ ከብረት ወይም ከነሃስ የሚሰራ የቤተክርስቲያን እጣን ማጨሻ፥ ሻኩራ።

ፅንሃህ

ፅንስ "ፀነሰ" ስር ተመ.

ፅንፍ "ጠንፍ" ስር **"ጥንፍ"** ን ተመ.

ፅዋ(ጥዋ) ስ 1. ከሸክላ ወይም ከቀንድ፥... የሚሰራና ለመጠጫ የሚያገለግል እቃ። 2. በመላእክት፥ በሰማእታት ፥... ስም ማህበር የሚጠጡ ምእመናን በፀበል መልክ የተዘጋጀውን ጠላ የሚኾሙበት ትንሽ ገንቦ። 3. በመላእክት፥ በሰማእታት፥... ስም የሚጠጣ ማህበር። 4. (ዘይ.) እድል፥ እጣ፥ ፋንታ።

ፅዋውን አንሳ (በግብዣ ወቅት) መጠጥ የተቀዳበትን ብርጭቆ ወደላይ ከፍ አድርጎ በመያዝ ግብዣው ለተካሄደበት ጉዳይ ያለውን ድጋፍ፥ ደስታ፥...ገለፀ።

ፅዋው ሞላ እድሜው ደረሰ፥ የተወሰነው የግፍ ጊዜ አለቀ። *ፅዋው ሲሞላ ሁሉም የሰራውን ያገኛል።*

ፅዱ "ፀዳ"ስር ተመ.

ፅዳት ዝ.ከ.

ፅድ "ጥድ"ን ተ.መ.

ፅድቅ "ፀደቀ¹"ስር ተመ.

ፅጌ ስ 1. የአበባ ወቅት፤ "ወርሃፅጌ" ም ይባላል። 2. (ኢ.ኦ.ተ.ቤ .) ቅድስት ድንግል ማርያም ልጇን ይዛ ወደ ግብፅ የተሰደደችበትን ጊዜ በማሰብ ከመስከረም 26 እስከ ህዳር 6 ቀን የሚደረግ የፆም፥ የፀሎትና የማህሌት ወራት።

ፅጌረዳ ስ የተለያየ ቀለምና ጥሩ መአዛ ያለው የአበባ አይነት፤ ተክሉም ፅጌረዳ ይባላል።

ፆ የ"ፀ" ፊደል ሳብእ ዘር።

ፆመ(ጠመ) ግ 1. ሃይማኖታዊ በሆነ ምክንያት ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ሰአት መብላትና መጠጣት ተወ፡ ከምግብ ተቆጠበ። 2. በስርአተ ሃይማኖት ምክንያት ለተወሰኑ ቀናት ስጋ፥ ቅቤ፥ ወተት፥... ከመመገብ ተቆጠበ።

ፆም ስ 1. ሃይማኖታዊ በሆነ ምክንያት ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ሰአት መብላትና መጠጣት ፈፅሞ ሙሉ በሙሉ መተው ወይም የተወሰኑ የምግብ አይነቶችን፥ ተግባሮችን፥ ... መተው።2. ፆም የሚፆምበት ጊዜ፥ ወቅት።

ፆሙን (ጠሙን) ዋለ ምግብ ሳይቀምስ ዋለ።

ፆም ሻረ 1. *ፆም መፆሙን ትቶ ወይም ዘንግቶ ያለሰአቱና ያለ ጊዜው በላ።*2. *በፆም ጊዜ የፍስክ ምግብ በላ።*

ፆም ያዘ *መፆም ጀመረ።*

የፆም ምግብ ስ እንደ ስጋ፥ ቅቤ፥ ወተትና እንቁላል፥... ያሉትን የማይጨምር የምግብ አይነት።

የፆም ቆሎ ስ 1. የሁዳዴ ፆም ሲያልቅ ለነፍስ አባት የሚሰጥ እህል ወይም ዱቄት፥...። 2. በፆም ጊዜ ምእመናን ለካህናት የሚሰጡት ቆሎ(በገጠር አካባቢ)። 3. ቀደም ሲል በነበረው ስርአት በፆም ጊዜ ገባር ለሹም ወይም ለባለርስት ይሰጠው የነበረ የቆሎ እህል።

የፆም ወጥ ስ 1.ስጋ ወይም ቅቤ የሌለው ወጥ። 2. (ዘይ.) ችኮ፥ ለዛ የሌለው (ሰው)።

ፆመ ድጓ ስ 1. በሁዳዴ ፆም ጊዜ በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚዘመር ያሬዳዊ ድርሰት። 2. ከላይ የተጠቀሰውን ዜማ የያዘ መፅሃፍ።

ፆመኛ ስ የፆምን ስርአት ተከትሎ የሚፆም ሰው።

ጿሚ ዝ.ከ.

ፆታ ስ ወገን (የእንስት ወይም የተባእት)።

ጿ የ"ፀ" ፊደል ፍንፅቅ ዘር።

ጿሚ "ፆመ" ስር ተመ.

ፈ

ፈ ከ "ፀ" ፊደል ዘር ቀጥሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል (ግእዙ ሆሄ) ።

ፈለመ ግ 1. ቀድሞ መጣ ወይም ወጣ። *ውሃ ለቀደመ ግዳይ ለፈለመ።* 2. ተለመ፣ አንድ ፈር ቀደደ (ለእርሻ)።

ፍልሚያ ስ 1. ትግል፣ ግብግብ፣ ውጊያ። 2. ጥል፣ አምባጓሮ።

ፍልም ስ ትልም።

ተፋለመ ግ ትግል፣ ግብግብ፣ ውጊያ ገጠመ።

ተፋላሚ ቅ ባላንጣ፣ ተፎካካሪ (በትግል፣ በውጊያ)።

ፈለሰ ግ 1. ተሰደደ፣ አገሩን ጥሎ ሄደ። 2. ተነቀለ፣ ተመነገለ፣ ተፈነቀለ።

መፍለስ ቅ 1. ጥርስ ሸረፋ፣ ወላቃ። 2. ከራንቻ ጥርሱ ወልቆ በፊት በኩል ከታችና ከላይ ሁለት ጥርስ ያለው (በቅሎ)።

ፈላሻ ስ 1. ይኖርበት የነበረውን አገር ለቆ በመሄድ በሌላ አገር የሚኖር ህዝብ 2. ቤተ እስራኤል።

ፍልሰልስ ቅ የወላለቀ፣ የፈራረሰ።

ተፋለሰ ግ 1. ተለዋወጠ፣ በተባለው ጊዜ ሳይሆን ቀረ። *ለሱ በመቅረቱ ፕሮግራማችን ተፋለሰ።* 2. ተበታተነ፣ ተለያየ፣ ተዘበራረቀ (አንድ ላይ የነበረ፣ በስርአት የተቀመጠ ወይም ተመሳሳይ የነበረ ነገር)።3. ተቧቀሰ፣ ተደባደበ።

አፈለሰ ግ 1. ነቀለ፣ አወለቀ። 2. ነቅሎ ወይም አንስቶ ወደ ሌላ ቦታ ወሰደ። 3. መታ። *በቡርኩም አፈለሰው።*

አፋለሰ ግ 1. በታቀደው ወይም በተወሰነው ጊዜ እንዳይሆን አደረገ። 2. አዘበራረቀ፣ በታተነ (በአንድ ላይ፣ በስርአት የተቀመጠን ወይም ተመሳሳይ የነበረን ነገር)። 3. አጣላ፣ እንዳይስማሙ አደረገ።

ፈለሰመ "**ፈለሰፈ**"ን ተመ.

***ፈለሰሰ**

ፈልሳሳ(ፈለስስ) ቅ በምቾት ወይም በድሎት ያለ፣ ደስተኛ።

ተንፈላሰሰ ግ ተመቸው፣ ደላው ወይም ተንደላቀቀ።

አንፈላሰሰ ግ እንዲመቸው ወይም እንዲደላው አደረገ፣ አንደላቀቀ።

ፈለሰፈ(ፈለሰመ) ግ በምርምር ወይም በጥናት አዲስ ነገር ሰራ፣ አገኘ።

ፈላስፋ (ፈላስማ) ስ 1. የፍልስፍና ሰው። 2. አንድን ነገር ለመጀመሪያ ጊዜ የሰራ፣ የፈጠረ፣ ያገኘ ሰው። 3. ጥበበኛ፣ አዋቂ፣ ተመራማሪ።

ፈልሳፊ ቅ አንድን ነገር ለመጀመሪያ ጊዜ የሰራ፣ ያገኘ፣ የፈጠረ።

ፍልስፍና ስ 1. ስለ ተጨባጩ አለም እውነታ፣ በተለይም የተፈጥሮን አመጣጥ፣ ምክንያትና ምንነት እንዲሁም ይህ ሁሉ ነገር የሚመራበትን ስርአትና እውነት ለማወቅ ወይም ለማግኘት ጥናት የሚያደርግ የእውቀት ዘርፍ። 2. በተራ ቁጥር አንድ በተጠቀሰው የእውቀት ዘርፍ መሰረት በአንድ ነገር ላይ በተደረገ ጥናትና ምርምር አማካኝነት የሚገኝ ግንዛቤ፣ እምነት፣ እውቀት፣ የሰረፀ አተያይ ።

ተፈለሰፈ ግ በምርምር አንድ አዲስ ነገር ተሰራ፣ ተፈጠረ።

ተፈላሰፈ ግ ተመራመረ፣ ተራቀቀ።

ተፈላሳፊ ስ ተመራማሪ።

አፈላሰፈ ግ አመራመረ።

ፈለቀ ግ 1. ከስር ወደላይ ወጣ፣ ፈሰሰ፣ መነጨ (ለምሳሌ ምንጭ)።2. ብልጭ አለ፣ በረቀ፣ አንፀባረቀ (ብርሃን)።

ፍልቅ አለበት አቀረሸው (ህፃን)።

ፍላቂ ቅ ሙሉ ፈሳሽ ከያዘ ብርጭቆ፣ ጠርሙስ፣...ላይ በትንሹ ቡልቅ ብሎ የሚፈሰው ፈሳሽ።

ፍልቅልቅ ቅ ፊቱ ላይ ፈገግታ ወይም የደስታ ስሜት የሚታይበት።

ፍልቅልቅ አለ ግ ተፍለቀለቀ።

ተፍለቀለቀ ግ 1 . በጣም ፈላ፣ ተንተከተከ። 2. ፊቱ በደስታ በራ፣ ተደሰተ፣ ፈነደቀ።

አፈለቀ ግ 1. አወጣ፣ አመነጨ (ውሃን)። 2. ከራሱ (ከአእምሮው) አንቅቶ ወይም አመንጭቶ አቀረበ። *አዲስ ሃሳብ አፈለቀ።*

ፈለቀቀ ግ 1. የተጣበቀ ነገርን ለየ፣ ከፈለ፣ ፈረቀቀ። 2. የጥጥ ፍሬን ለማውጣት ፍንድን አላላ። 3. የጥጥ ፍንድን እያላላና ፍሬውን ከውስጡ እየፈለገ አወጣ።

ፍልቃቂ ቅ ከተያያዘ ወይም ከተጣበቀ ወይም ድፍን ከሆነ ነገር ውስጥ ተለይቶ ወይም ተከፍሎ የወጣ አንዱ ክፍል። *የብርትኳን ፍልቃቂ።*

ፍልቅቅ ቅ 1. ፍሬውን ለማውጣት እንዲያመች ተብሎ የላላ (የጥጥ ፍንድ)። 2. ተያይዞ ወይም ተጣብቆ የነበረና በኋላም በከፊል የተላቀቀ፣ የተሰነጠቀ።

ተፈለቀቀ ግ 1. ተያይዞ ወይም ተጣብቆ የነበረው በከፊል ተላቀቀ፣ ተሰነጠቀ። 2. የጥጥ ፍንድ፣ የአበባ እምቡጥ፣... ሽፋኑን ሰንጥቆ

ወይም ፈልቅቆ ወጣ (ወደውጭ)።

ፈለቀጠ ግ ከፈለ፡ ገመሰ፣ ፈለቀቀ (ሎሚን፣ ብርቱካንን፣..)።

ፍልቃጭ ቅ ክፋይ፣ ግማሽ፣ ፍንካች።

***ፈለከለከ**

ፍልክልክ አለ ግ ተፍለከለከ።

ተፍለከለከ ግ በብዛት ተንቀሳቀሰ፣ ተላወሰ፣ ተርመሰመሰ (ትላትል፣ ነፍሳት)።

አፍለከለከ ግ አርመሰመሰ።

ፈለገ ግ 1. ሻ፣ ወደደ፣ ፈቀደ። 2. የጠፋን ወይም አስፈላጊ የሆነን ነገር ለማግኘት ሞከረ፣ ጣረ።

ፍለጋ ስ የጠፋን ወይም የሚያሻን ነገር ለማግኘት የሚደረግ ሙከራ፣ ጥረት።

ፍላጎት ስ አንድ ነገር ለማድረግ፣ ለማግኘት፣ ለመሆን የመሻት ስሜት።

ተፈለገ ግ አስፈላጊ ሆነ።

ተፈላጊ ቅ 1. ጠቃሚ፣ ተገቢ፣ ተስማሚ። *ሸንተራ ለክረምት ተፈላጊ እቃ ነው።* 2. ተወዳጅ። *የኢትዮጵያ ቡና በጣም ተፈላጊ ነው።*

ተፈላለገ ግ 1. ተጠያየቀ፣ ተሳሰበ። 2. አንዱ ሌላውን ለማግኘት ጣረ። 3. ፈለገ። *እስኪ በአካባቢህ የሚሸጥ ቤት እንዳለ ተፈላለግልኝ።*

ተፈላሰጉ 1. ተዋደዱ(ተቃራኒ ፆታዎች በፍቅር)። 2. ለፀብ፣ ለግድያ ተሳሰቡ።

አፈላለገ ግ አንድን ነገር ለማግኘት በየቦታው፣ በየአቅጣጫው ፈለገ ወይም አጠያየቀ።

አፋለገ ግ የጠፋ ነገር ለማግኘት በሚደረግ ፍለጋ ረዳ፣ ተባበረ።

አስፈለገ ግ 1. ተፈላጊ፣ ጠቃሚ ሆነ። 2. አማረ። *አዲስ ልብስ አስፈለገኝ።* 3. አንድ ነገር መሆን፣ መደረግ፣ መገኘት፣... እንዳለበት ግድ ሆነ።

አስፈላጊ ቅ ጠቃሚ፣ ተፈላጊ።

ፈለግ ስ 1. ከእጅና እግር ጣት እንዲሁም ከተረከዝ ላይ እየተላጠ የሚነሳ ቆዳ። 2. መሬት ላይ የሚያርፈው የኮቴ፣ የጫማ፣ የእግር ቅርፅ፤ ዱካ። 3. አርአያ፣ ምሳሌ። *የወንድሙን ፈለግ ተከትሎ ሃኪም ሆነ።*

ፈለጠ ግ 1. ሰነጠቀ፣ ገመሰ፣ ሸነሸነ (ለምሳሌ እንጨትን)። 2. ተረከከ፤ በዱላ መታ (ጭንቅላትን)። 3. በጣም አመመ (ራስ ምታት)።

ፈላጭ "እንጨት ፈላጭ" ን ተመ.

ፈላጭ ቆራጭ 1. አምባገነን፤ በህዝብ ፍላጎትና ፈቃድ ሳይሆን እንዳሻው የሚመራ ወይም የሚያስተዳድር (መሪ፣ መንግስት)። 2. ሌሎችን በመጫን ራሱ እንደፈለገው ብቻ ማንኛውንም የሚያደርግ።

ፍላጭ ስ የፍልጥ ስንጣሪ፣ ቁራጭ።

ፍልጥ ስ የተሰነጣጠቀ፣ የተፈላለጠ እንጨት።

ፍልጥ ያህላል ትልቅ ነው (ብዙውን ጊዜ ለጥርስ)።

ፈለፈለ^{1} ግ 1. ቦረቦረ፣ ሰረሰረ። 2. በተነባበረ ወይም በተጠጋጋ ነገር ስር ወይም መካከል ሰርስሮ ለመግባት ታገለ። 3. ፍሬን ከሽፋኑ፣ ከቆረቆንዳው ለየ፤ ጠረጠረ።

ፈልፍሎ አወጣ (የተደበቀ ነገርን፣ ምስጢርን፣...) ፈልጎ ወይም ተከታትሎ ይፋ አወጣ።

ፈልፈላ ቅ 1. ተንኮለኛ፣ ሸረኛ። 2. የተደበቀ ነገር የማያመልጠው፣ ሰርሳሪ።

ፍልፍል ቅ ከእንቁረባው ወይም ከቆረቆንዳው የተላቀቀ የባቄላ፣ የበቆሎ፣...ፍሬ።

ፈለፈለ^{2} ግ ብዙ ልጅ ወለደ።

ፈለፈለች ዶሮ ወይም ወፍ ለታቀፈችው እንቁላል ሙቀት በመስጠት ጫጩት እንዲወጣ አደረገች።

ፍልፍል ቅ ከእንቁረባው ወይም ከሽፋኑ የተላቀቀ የባቄላ፣ የበቆሎ፣... ፍሬ ።

ተፈለፈለ ግ ተቀፈቀፈ፣ ጫጩት ከእንቁላል ውስጥ ወጣ።

ፈሊጥ ስ 1. በምሳሌ፣ በንፅፅር፣ በተረትና ምሳሌ፣... አማካኝነት የሚቀርብና ስሜትን የሚስብ የአነጋገር ዘዴ፤ ዘይቤ። 2. የባህርይ፣ የልማድ፣ የአሰራር ዘዴ።

ፈሊጣዊ አነጋገር ስ ሁለት ቃላት ለየብቻቸው ሆነው ሲነገሩ ከሚሰጡት ሃሳብ ውጪ በአንድ ላይ ሲጣመሩ የሚሰጡት የተለየ ሃሳብ (ለምሳሌ እጁ አጠረ፣ ልቡ ወለቀ፣ አይን አውጣ፣ ሆደ ሰፊ)።

ፈላ^{1} ግ 1. ተፍለቀለቀ፣ ተንተከተከ (እሳት ላይ የተጣደ ውሃ፣ ወጥ፣...) 2. ሲጠጣ ደረሰ (እሳትላይ የተጣደው ቡና ወይም ሻይ)። 3. (ጥንስስና እንኩሮ በአንድ ላይ በመሆን) ተብላላ።

ፈላበት የጥጋብ ወይም የጉርምስና ስሜት ተሰማው።

እንፋሎት ስ ከሚፈላ ውሃ ወይም ሌላ ፈሳሽ ነገር ላይ የሚወጣ ጭስ መሰል ነገር፤ ተን።

ፍላሎት ስ የታፈነ፣ የታመቀ የሃዘን ወይም የንዴት ስሜት።

ፍል ቅ በጣም የሞቀ ወይም የፈላ(ውሃ)።

ፍል ውሃ ስ በተፈጥሮ ከመሬት እየፈለቀ የሚወጣ ሙቅ ውሃ።

ፈላ^{2} ግ 1. በቀለ፣ ችግ አለ (ችግኝ)። 2. (ዘይ.) በብዛት ታየ፣ ቁጥሩ ጨመረ።

አፈሳ ግ ፍሬ ዘርቶ ችግኝ አበቀለ።

ፍል ስ ችግኝ።

ፈሳስግ "ፈሰሰፈ" ስር "ፈሳስፋ"ን ተመ.

ፈሳስፋ "ፈሰሰፈ" ስር ተመ.

ፈሳሽ " ፈሰሰ" ስር ተመ.

ፈሳጭ " ፈሰጠ" ስር ተመ.

ፈልሳሳ "*ፈሰሰሰ" ስር ተመ.

ፈልሳፊ " ፈለሰፈ" ስር ተመ.

ፈልፈላ " ፈለፈለ¹" ስር ተመ.

ፈረመ ግ 1. አንድን ፅሁፍ ህጋዊ ለማድረግና በይዘቱ መስማማቱን ለመግለፅ በፅሁፉ ግርጌ ስሙን ፃፈ፤ ፊርማውን አኖረ።2. (ዘይ.) በፊርማ አፀደቀ።*ስምምነቱን የፈረሙ ሃገሮች።*

ፊርማ ስ 1. አንድን ፅሁፍ ህጋዊ ለማድረግና ስምምነትን ለመግለፅ የሚመለከተው አካል በፅሁፉ መጨረሻ ላይ ከስም ጋር የሚኖረው የራሱ የሆነ የጣት አሻራ ወይም የፅሁፍ ምልክት። 2. ውል፤ ስምምነት።

ፊርማ ቀደዱ ተፋቱ፤ ጋብቻቸው ፈረሰ።

ተፈረመ ግ የፊርማ ምልክት ተደረገበት።

ተፈራረመ ግ በፅሁፍና በፊርማ ተዋዋለ (ለጋብቻ ወይም ለሌላ ጉዳይ)።

አፈራረመ ግ በፅሁፍና በፊርማ አዋዋለ።

***ፈረመረመ**

ፍርምርም ቅ ትጉህ፤ ተጣጣሪ።

ተፍረመረመ ግ ተፍጨረጨረ፤ ተጣጣረ።

አፍረመረመ ግ አፍጨረጨረ፤ አተጋ።

ፈረሰ ግ 1. ተናደ፤ ተፈነቃቀለ፤ እንዳልነበር ሆነ። 2. ተሻረ (ህግ፤ ስርአት፤ ውል፤ ደንብ)። 3. ተበተነ፤ ሳያልቅ ተቋረጠ (ስብሰባ)። 4. ሳይሆን፤ ሳይሳካ ቀረ። *ቀጠሮው ፈረሰ።* 5. ቅምጥና፤ ደረመን አጠቃው። *ሰውነቱ ፈረሰ ።* 6. በሰበሰ (ሬሳ)።

ፈራረሰ ግ ፈረሰ፤ ወዳደቀ፤ እንዳልነበር ሆነ።

ፈራሽ ቅ 1. ቋሚ ያልሆነ፤ ሟች። 2. ዘላቂነት የሌለው፤ ጊዜያዊ።

ፍራሽ ቅ ከፈረሰ ቤት ወይም አጥር ላይ የሚሰበሰብ እቃ (እንጨት፤ ቆርቆሮ፤...)።

ፍርስራሽ ዝ.ከ.

ፍርስ አለ ግ (ዘይ.) በጣም ሳቀ ወይም በጣም አለቀሰ።

ፍርስ አደረገ ግ (ዘይ.) በጣም አሳቀ ወይም በጣም አስለቀሰ።

ተፋረሰ ግ 1. ሳይስማማ ቀረ (በሃሳብ፤ በውል፤...)። 2. ከሸፈ፤ ሳይሳካ ቀረ።

አፈረሰ ግ 1. ናደ፤ ፈነቃቀለ፤ እንዳልነበር አደረገ። 2. ሻረ፤ ጣሰ። *ህግ አፈረሰ።* 3. ተቃወመ፤ አልስማማ አለ። 4. መድሃኒትነቱን እንዲያጣ አደረገ፤ አረከሰ። 5. ቅስናውን፤ ምንኩስናውን፤...ተወ፤ ህጉን ጣሰ፤ ስርአቱን ተላለፈ። 6. ቃል በገባበት ወይም በተስማማበት መሰረት ሳያደርግ ቀረ፤ ከዳ። 7. **ቀደም** ሲል የተነገረን ሃሳብ ትክክል እንዳልሆነ አሳየ ወይም አረጋገጠ ። *ቲዎሪውን አፈረሰ።*

አፍራሽ ቅ 1. ገንቢ ወይም ጠቃሚ ያልሆነ(ሃሳብ፤ ድርጊት)። 2. አሉታዊ (ሃሳብ ወይም አገላለፅ)።

አፈራረሰ ግ ናደ፤ አፈረሰ፤ እንዳልነበር አደረገ።

አፋረሰ ግ እንዳይሳካ፤ ስምምነት እንዳይኖር አደረገ።

ፈረሰኛ¹ ስ በደረት በኩል የሚገኝ የዶሮ ብልት።

ፈረሰኛ² "ፈረስ" ስር ተመ.

ፈረሱላ ስ አስራ ሰባት ኪሎ ያህል የሚመዝን የቡና፤ የበርበሬና የሌሎች ልዩ ልዩ ነገሮች ክብደት መለኪያ።

ፈረሳ ቤት ስ ሰውነት ላይ ችፍ ብሎ የሚወጣ የእከክ አይነት።

ፈረስ ስ 1. ከቤት እንስሳት አንዱ የሆነ፤ ለስላሳ ጋማና ጭራ እንዲሁም አራት እግሮች ያሉትና ለመጓጓዣ የሚያገለግል የጋማ ከብት (ስእሉን የቤት እንስሳ ስር ተመ.)። ቅ 2. (ዘይ.) ሀ. ረዥምና ግዙፍ የሆነ ሰው። ለ. ተጠንቅቆ የማይራመድ፤ ደንባራ (ሰው)።

የፈረስ ስም "አባ" የሚለውን ቃል እያስቀደመ የሚነገር፤ ፈረስ የመጋለብ ወይም የመቀመጥ ሞያ ወይም ችሎታ ላላቸው ነገስታት፤ መሳፍንት፤ መኳንንትና ጀግኖች የሚሰጥና የባለፈረሱን ጠባይ፤ ምኞት የሚገልፅ ስም፤ "አባ ታጠቅ"፤ "አባ ዳኘው" የመሳሰለው አይነት ስም።

የፈረስ ዘንግ ስ ግንዱ ውስጠ ክፍት ሆና ቅልጥም ያለው፤ በአናቱ አካባቢ ድብልብል የሆነ የአበባና የፍሬ መያዣ ኳስ መሰል ነገሮች የሚገኙበት አነስተኛ የእፅዋት አይነት፤ ራስ ክምር።

የፈረስ ጉልበት ስ 750 ያህል ኪሎ ዋት ጉልበት ያለው የሞተር ጉልበት መለኪያ።

ፈረሰኛ ቅ ፈረስ ግልቢያ አዋቂ ።

ፈረሰኛ ውሃ ስ በዝናብ ምክንያት ወንዝ በሚሞላበት ጊዜ ንፁህ የነበረውን የወንዝ ውሃ እያደፈረሰ ከዋናው የውሃው ሙላት ፊት ለፊት የሚጋልበው ድፍርስ ወይም ደራሽ ውሃ።

***ፈረቀ**

ፈረቃ ስ (የመማሪያ፤ የመስሪያ ጊዜ) ተራ፤

ወረፋ። *ተማሪዎቹ በፈረቃ ይማራሉ።*

ተፈራረቀ ግ አንድን ነገር በየተራ አደረገ፤ አንዱ ሲለቅ ሌላው ተተካ።

አፈራረቀ ግ ከአንዱ በኋላ ሌላውን ተካ፥ አለዋወጠ።

***ፈረቀረቀ**

ፍርቅርቅ ቅ በምጣድ ላይ እያለ ስለነፈሰበት የተሰነጣጠቀ፤ ፍርክርክ (እንጀራ ወይም ዳቦ)።

ተፍረቀረቀ ግ ተሰነጣጠቀ፥ ነቃ፥ ተፍረከረከ (ዳቦ፥ እንጀራ)።

አፍረቀረቀ ግ ፍርቅርቅ እንዲሆን አደረገ፤ አፍረከረከ።

ፈረቀቀ ግ ለያየ፥ ነጣጠለ፥ ፈለቀቀ።

መፈርቀቂያ ስ ሽብልቅ።

ተፈረቀቀ ግ ተፈለቀቀ፥ ተነጣጠለ፥ ተለያየ።

አፈራቀቀ ግ አለያየ፥ አራራቀ። *እግሩን አፈራቶ ቆሟል።*

ፈረቃ "*ፈረቀ" ስር ተመ.

***ፈረነሰ**

ፍርንስ (ፈርናሳ) ቅ ዘና ብሎ ወይም ተንፈላሶ የሚተኛ፥ የተኛ።

ፍርንስ አለ ግ ተፈረነሰ።

ተፈረነሰ ግ ዘና ብሎ ወይም ተንፈላሶ ተኛ።

ፈረንጅ ስ የቆዳው ቀለም ነጭ የሆነ የውጭ አገር ሰው።

***ፈረከረከ**

ፍርክርክ(ፈረክራካ) ቅ 1. የሚፈረፈር፥ የሚሽራረፍ። 2. ፈራ፥ ቡከን።

ፍርክርክ አለ ግ ተፍረከረከ።

ተፍረከረከ ግ 1. ተሸራረፈ፤ ተፈረፈረ። 2. መበታተን፤ መለያየት፥ መፈራረስ፥… ጀመረ (አንድ አይነት አላማ ወይም ሃሳብ የነበረው የፖለቲካ ድርጅት፤ ቡድን፤…)። 3. በፍርሃት ተርበተበተ፤ ተርበደበደ።

አፍረከረከ ግ 1. ሸራረፈ፥ ፈረፈረ። 2. መለያየት፥ መበታተን እንዲፈጠር አደረገ (አንድ አይነት አላማ ወይም ሃሳብ በነበረው የፖለቲካ ድርጅት፥ ቡድን፥…መካከል)።

ፈረከሰ ግ 1. ገመሰ፥ ሰነጠቀ። 2. አደቀቀ፥ ሰባበረ (ለምሳሌ ድንጋይን)። 3. ፈነከተ፤ አቆሰለ (ራስን)።

ፈርካሳ ቅ (ስድብ) በርጋዳ፥ እግሯን አፈራቃ፥ በርግዳ የምትቀመጥ (ሴት)።

ፍርክስ ቅ የተገመሰ፥ የተሰነጠቀ።

ፍርክስክስ አለ ግ ፍርስርስ አለ (ለምሳሌ የተቀቀለ ድንች፥ ባቄላ፥… በጣም ከመብሰሉ የተነሳ)።

ተፈረከሰ ግ ተገመሰ፥ ተሰበረ።

ተፈረከሰች ግ (የጥላቻ አነ.) ብርግድ ብላ፥ እግሯን አፈራቃ ተቀመጠች።

ተፈረካከሰ ግ ፍርክስክስ አለ።

***ፈረከከ**

ፈርካካ ቅ በፍርንትቱ አካባቢ ቁስል እንዳለበት ሁሉ ጭንና ጭኑ የማይጠጋጋ፥ የተራራቀ፥ በርጋዳ።

ፈርከክ አለ ግ ተንፈራከከ።

ፈርከክ አደረገ ግ አንፈራከከ።

ተንፈራከከ ግ ተራራቀ፥ ተለያየ፥ ተበረገደ (ለምሳሌ ጭንና ጭን)።

አንፈራከከ ግ አራራቀ፥ ለያየ፥ በረገደ (ለምሳሌ ጭንና ጭንን)።

ፈረክራካ "*ፈረከረከ" ስር "ፍርክርክ"ን ተመ.

***ፈረዘዘ**

እንፍርዝ ቅ 1. ሆዱ የሞላ፥ የጠገበ። 2. (ዘይ.) ዘና፥ ረጋ ያለ።

ፈርዛዛ (ፈረዝዝ) ቅ 1. ዝ.ክ። 2. (ዘይ.) ደስተኛ የሆነ፥ ሰላም ወይም ርጋታ ያለው።

ፍርዝዝ አለ ግ ተንፈረዘዘ።

ተንፈረዘዘ ግ 1. ጠገበ፥ ሆዱ ሞላ። 2. (ዘይ.) ተደሰተ፤ ሰላም፤ እርካታ ወይም ርጋታ አገኘ፤ ተዝናና።

አንፈረዘዘ ግ 1. አጠገበ። 2. አስደሰተ። 3. ዘና፥ ረጋ አደረገ።

ፈረደ ግ 1. ፍርድ፥ ውሳኔ ሰጠ። 2. ጥፋተኛ አደረገ። *ሰዉ በሱ ላይ ፈረደ።* 3. ባለውቃቢ ውቃቢዬ ነገረኝ የሚለውን መልስ ለጠያቂዎቹ (ለአስጠንቋዮቹ) ተናገረ።

ፈረደበት መጥፎ ወይም ክፉ ነገር አጋጠመው ወይም ደረሰበት።

የፈረደበት መከረኛ፥ ያልታደለ።

ፍረደኝ ጉዳዩን አይተህና ተመልክተህ ውሳኔ ወይም ዳኝነት ስጠኝ። *ህዝብ ፍረደኝ።*

ፍርደኛ ቅ ለፈፀመው ጥፋት በፍርድ ቤት ተፈርዶበት ወህኒ ቤት በእስር ላይ የሚገኝ።

ፈራጅ ስ ፍርድ ወይም ውሳኔ ሰጪ፥ ዳኛ።

ፍርድ ስ የዳኛ ወይም የፍርድ ቤት ውሳኔ።

ፍርደ ገምድል ትክክለኛ ያልሆነ ወይም አድሉአዊ ፍርድ የሚፈርድ።

ፍርዱ ቀጠነ ፍርዱ ተዛባ፥ ተጓደለ።

ፍርድ ሸንጎ ስ በቀበሌና በገበሬ ማህበራት ውስጥ ከነዋሪው ህዝብ መሃል ተመርጦ የዳኝነትን

ስራ ያከናውን የነበረ ኮሚቴ (ከ1966 አብዮት ወዲህ እስከ 1983 ዓ.ም.)።

ፍርድ ቤት ስ ዳኞች ፍርድ የሚሰጡበት፣ የዳኝነት ስራ የሚከናወንበትና ህግ የሚተረጎምበት መስሪያ ቤት።

ፍርጃ ስ መጥፎ አጋጣሚ፣ ጣጣ፡ ችግር።

ተፈረደ ግ ፍርድ ተሰጠ፣ ተበየነ።

መፋረጃ (መፍረጃ) አደረገ ግ ሰው እንዲወቅሰው ወይም እንዲፈርድበት አደረገ።

ተፋረደ ግ ጉዳዩን ለፍርድ አቀረበ።

ይፋረደዋል ሳደረሰው በደል፣ግፍ፣... ይከሰዋል ወይም ለፍርድ ያቀርበዋል።

ተፋራጅ ቅ ተከራካሪ፣ ከሳሽ።

አስፈረደ ግ ጉዳዩ ወይም ክሱ እሱን በሚጠቅም ሁኔታ እንዲፈረድ አደረገ።

ፈረድ ስ ውሃ የሸረሸረው ፈፋ፣ ጉድባ።

ፈረጀ ግ በአንድ የተወሰነ መመዘኛ ወይም መለኪያ መሰረት በአይነት በአይነቱ፣ በመልክ በመልኩ፣.. ከፋፈለ፣ ለየ፡ መደበ።

ፈርጅ ስ 1. ወገን፣ ክፍል፣ መደብ። 2. የሸማ አንዱ አርብ (ለምሳሌ አንድ ነጠላ ሁለት ፈርጅ አንድ ጋቢ ደግሞ አራት ፈርጅ ሸማ ይኖረዋል)።

***ፈረገረገ**

ፍርግርግ አለ ግ ተፍረገረገ።

ተፍረገረገ ግ ተንፈራገጠ።

አፍረገረገ ግ አንፈራገጠ።

***ፈረገጠ**

ፍርግጥ ፍርግጥ አለ ግ ተፈራገጠ።

ተፈራገጠ (ተንፈራገጠ) ግ ተጋድሞ ወይም ተኝቶ እግሩን በማጠፍ፣ በመዘርጋት ወይም በማወራጨት ወዲያና ወዲህ ተንቀሳቀሰ፣ ተወራጨ (በህመም፣ በቅዠት፣... ምክንያት)።

አፈራገጠ (አንፈራገጠ) ግ ተጋድሞ ወይም ተኝቶ እግሩን ወዲያ ወዲህ በማንቀሳቀስ፣ በማጠፍ በመዘርጋት፣... አንቀሳቀሰ፣ አወራጨ (በህመም፣ በቅዠት፣... ምክንያት)።

ፈረጠ^{1} ግ 1. ውስጡ የነበረው ፈሳሽ ፈንድቶ ወጣ፣ ፈሰሰ (ለምሳሌ ጡት፣ ቁስል፣ እባጭ)። 2. ተሰብሮ ወይም ተጨፍልቆ በውስጡ ያለው ፈሳሽ ፈሰሰ (እንቁላል፣ ቲማቲም፣...)። 3. (ዘይ.) ወጣ፣ ይፋ ሆነ (እውነቱ)። 4. ጠፋ፣ ፈሰሰ (አይን)።

ፍርጥ ብትል ፈፅሞ፣ በጭራሽ፡ ምንም ቢሆን ለማለት የሚያገለግል አገላለፅ። *ፍርጥ ብትል ገንዘብ አይሰጥህም።*

ፍርጥርጥ አለ ግ 1. በውስጡ ያለው መግል፣ ፈሳሽ ወጣ፡ ነፈረቀ (ቁስሉ)።2. ወጣ፣ ገልፅልፅ አለ (እውነቱ)።

ተፍረጠረጠ ግ 1. መግሉ፣ ፈሳሹ እንዲወጣ ተደረገ፣ ነፈረቀ (ቁስሉ)። 2. ወጣ፣ ይፋ ሆነ (እውነቱ)።

አፍረጠረጠ ግ 1. አድፈጠፈጠ፣ አመገለ (ቁስሉን)። 2. ይፋ አውጥቶ ተናገረ (እውነትን)።

ፈረጠ^{2} ግ ወደቀ፣ ተፈጠፈጠ።

አፈረጠ ግ ጣለ፣ ከሰከሰ፣ ፈጠፈጠ።

ፈረጠመ ግ ዳበረ፣ ወፈረ፣ ጠነከረ (ሰውነት)።

ፍርጥም (ፈርጣማ) ቅ ሰውነቱ የዳበረና የጠነከረ።

ፍርጥም ያለ ዝ.ክ.

አፈረጠመ ግ 1. ፈረጠመ። 2. ፈርጣማ እንዲሆን አደረገ።

ፈረጠጠ ግ 1. ሸመጠጠ፡ ሮጠ። 2. ሸሸ።

ፈርጣጭ ቅ 1. ከፍርሃት የተነሳ የሚሮጥ፣ የሚሸሽ። 2. ኮብላይ።

***ፈረጠጠ**

ተንፈራጠጠ ግ እግሮቹን አራርቆ፡ በጣም ከፍቶ ቆመ ወይም ተቀመጠ። *ሰውየው ተንፈራጦ ቆመ።*

አንፈራጠጠ ግ እግሮቹን አራርቆ፣ በጣም ከፍቶ ቆመ ወይም ተቀመጠ *እግሮቹን አንፈራጦ ቆሟል።*

ፈረፈረ ግ 1. እንጀራ ወይም ዳቦ ቆራርሶ ወጥ ወይም ቁሌት ውስጥ በመፈትፈት ፍርፍር አዘጋጀ።2. በትንንሹ ቆራረጠ፣ ቆራረሰ (ዳቦን እንጀራን)። 3. ሸረሸረ፣ ቦረቦረ።

ፈረፈር ስ ጎርፍ የቦረቦረው ወይም የሸረሸረው መሬት።

ፍርፋሪ ስ 1. ተበልቶ የተረፈና የነኳኮተ ወይም የተቆራረሰ እንጀራ፣ ዳቦ፣ ትርፍራፊ። 2. ከተቆረሰ ዳቦ፣ ኬክ፣... ላይ ከስር የሚቀረው የደቀቀ ቁርስራሽ።

ፍርፍር ስ እንጀራ ቆራርሶ ቀጠን ባለ ወጥ፣ መረቅ ወይም ቁሌት ውስጥ በመጨመርና በመጠኑ ደረቅ አድርጎ በመፈትፈት የሚዘጋጅ ምግብ።

ተፈረፈረ ግ 1. ተቆራረሰ፣ ደቀቀ። 2. ተቦረቦረ፣ ተሸረሸረ።

***ፈረፈረ**

ፍርፍር አለ ግ ተንፈራፈረ።

ተንፈራፈረ ግ ተንፈራገጠ፣ ተወራጨ፣ ተንደፋደፈ።

አንፈራፈረ ግ አንፈራገጠ፡ አወራጨ፣ አንደፋደፈ።

ፈረፈር "ፈረፈረ" ስር ተመ.

ፈረፋንጎ (ፋራፋንጎ) ስ ለጭቃ መከላከያነት የሚያገለግልና የመኪናን፣ የብስክሌትን፣... ጎማ በከፊል የሚሸፍን ቀጭን ብረት ወይም ቆርቆሮ።

ፈሪሳዊ ቅ ከንቱ ውዳሴ ወዳጅ፤ እንዲህ ሰራሁ፣ አደረግሁ፣... መባልን የሚፈልግ፤ መመካሸት፣ መመጻደቅ የሚሻ፤ ግብዝ።

ፈራ ግ 1. ተርበደበደ፣ ተንቀጠቀጠ፣ ተሸበረ (ከአደጋ፣ ከጭንቀት፣ ከሚያስፈራ ነገር የተነሳ)። 2. ድፍረት አጣ። *መናገር ፈራ።* 3. ሰጋ፣ ጠረጠረ። *ከስራ ያባርሩኛል ብሎ ፈራ።* 4. አከበረ፣ ታዛዥ ሆነ። *እግዚአብሄርን ይፈራል።* 5. አፈረ፣ ተሸኮረመመ። *የሰው ዓይን ፈራ።*

ሲፈራ ሲቸር ሳድርግ ሳላድርግ በማለት እያመነታ።

ፈራ ተባ አለ ሳድርግ ሳላድርግ በማለት አመነታ፣ መድፈር አቃተው።

ፈሪ ቅ 1. ጀግንነት የሌለው፣ ቡከን። 2. ድፍረት የሌለው። 3. አይነአፋር።

ለ ___ ፈሪ ለ ___ አንድ የጎደለው (ለምሳሌ ለመቶ አንድ ፈሪ ማለት ዘጠና ዘጠኝ ማለት ነው)።

ፈሪሃ እግዚአብሄር እግዚአብሄርን መፍራት።

ፍርሃት (ፍራት፣ ፍራቻ) ስ 1. የመረበሽ ስሜት። 2. ስጋት፣ ጥርጣሬ። 3. ድፍረት የማጣት ስሜት። 4. አይነ አፋርነት።

ፍርሃት ፍርሃት አለው ግ 1. ባባ፣ ተረበሸ። 2. ድፍረት አጣ።

ተፈራ ግ 1. የሚያሰጋ፣ የማይደፈር ሆነ። 2. ተጠረጠረ፣ አስጊ ይሆናል ተብሎ ተገመተ። 3. ታፈረ፣ ተከበረ።

አስፈራ ግ አሰጋ፣ ጥርጣሬ ፈጠረ።

አስፈሪ ቅ 1. የፍርሃት፣ የጭንቀት ስሜት የሚያሳድር ወይም የሚፈጥር። 2. አስከፊ።

አስፈራራ ግ 1. የፍርሃት ስሜት ፈጠረ፣ አስጨነቀ። 2. ዛተ።

ማስፈራሪያ ፊት በጣም አስቀያሚ ፊት።

***ፈራ**

ፍሬ ስ 1. ተክል ከአበበ በኋላ ከአበባው ወይም ሊበላ ወይም የተለያየ ጥቅም ሊሰጥ ከሚችለው የተክሉ ክፍል ውስጥ የሚገኘውና በሂሳም ተመልሶ ሲዘራ የሚበቅለው የተክል ቅንጣት፣ ዘር። 2. የአንድን ተክል ዘር በውስጡ ይዞ የሚገኘውና ሊባው አካሉ የሚበላው ክፍል (ለምሳሌ የብርትኳን፣ የወይን፣ የሾላ፣... ፍሬ)። 3. (ዘይ.) ሀ. ቁም ነገር። *ንግግሩ ፍሬ የለውም።* ለ. መልካም ውጤት። *በስራችን ለፍሬ በቅተናል።* 4. ልጅ፣ ዘር። *ትወደው ከነበረ ባሏ ፍሬ ሳታገኝ ቀረች።* 5. ፍሬ የሚመስል ቅርፅ ያለውና ወንዱ ዘር የሚጠራቀምበት የአባለዘር ክፍል።

ፍራፍሬ ስ እንደ ብርትኳን፣ ፓፓያ፣ ሙዝ፣... ያሉ የሚበሉ የተክል ፍሬዎች። ...

ፍሬ ሰሞንኛ ቅ (ኢ. ኦ. ተ. ቤ.) የሳምንቱ ተረኛ ዲያቆን (በተወሰነው ሰአት ቤተክርስቲያንን በመክፈትና በመዝጋት፣ የቁርባን ህብስት በማዘጋጀት፣... አገልግሎት የሚሰጥ)።

ፍሬ ሰው ስ ዋና፣ ቁምነገረኛ ሰው።

ፍሬቢስ ቅ ቁምነገር የሌለው፣ ከንቱ።

ፍሬ ነገር ስ ዋና፣ ቁም ነገር።

ፍሬከርስኪ (ፍሬፈርስኪ) ቅ የማይረባ፣ ቁምነገር የሌለው።

ፍሬ ግብር ስ ዋና፣ አይነተኛ ግብር።

ፍሬያማ ቅ 1. ብዙ ፍሬ ያለው። 2. ጥሩ ውጤት ያለው።

አፈራ ግ 1. ፍሬ ያዘ ወይም አወጣ። 2. አስገኘ፣ አወጣ። *ዩኒቨርሲቲው ብዙ ምሁራንን አፈራ።* 3. ወለደ። *ብዙ ልጆች አፈራ።* 4. አገኘ (ለምሳሌ ገንዘብን)።

ፈራረሰ "ፈረሰ" ስር ተመ.

ፈራሽ ዝ.ከ.

ፈራጅ "ፈረደ" ስር ተመ.

ፈር ስ 1.ማረሻ በንቅቆ የሄደበት የእርሻ መስመር፣ ትልም። 2. ስርአት፣ መስመር።

ፈር ያዘ መስመር፣ ስርአት ያዘ።

ፈርስ ስ 1.በጨጓራ ውስጥ የሚገኝ የተፈጨና የቀጠነ የምግብ ጥርቅም። 2. ሆድ፣ ከርስ። 3.በውስጠኛው በኩል የሚገኘው የልብስ ወይም የጨርቅ መልክ።

ፈርሳም ቅ (ስድብ) ቀፈታም፣ ቦርጫም።

ፈርናሳ "*ፈረነሰ" ስር "ፍርንስ"ን ተመ.

ፈርካሳ "ፈረከሰ" ስር ተመ.

ፈርካካ "*ፈረከከ" ስር ተመ.

ፈርዛዛ "*ፈረዘዘ" ስር ተመ.

ፈርጅ "ፈረጀ" ስር ተመ.

ፈርጣማ "ፈረጠመ" ስር "ፍርጥም"ን ተመ.

ፈርጣጭ "ፈረጠጠ" ስር ተመ.

ፈርጥ ስ ከተለያዩ የከበሩ ድንጋዮች የሚሰራና በቀለበት፣ በዘውድ፣... ላይ የሚደረግ የሚያብለጨልጭ ጌጥ።

ፈሰሰ ግ 1. ተደፋ፣ ተከነበለ። 2. ተነገረ፣ ተገለፀ። *ትዝታው ፈሰሰ።* 3. ምቾት ወይም ድሎት ባለበት ሁኔታ ተጓዘ። *በመኪና እየፈሰሰ መጣ።* 4.ተጨመረ፣ ተደረገ። *እርሻው ላይ ፍግ*

ፈሰዘበት፡5. ወጣ (ለምሳሌ. ዘር ከወንድ ብልት)። 6. በብዛት ሆኖ ታየ ወይምወጣ። *ሰዉ ሜዳ ላይ ፈስሷል/የፈሰሰው ገንዘብ ትንሽ አይምሰልህ።*

ፈሰስ ስ 1. በዝናብ ጊዜ ከጣሪያ የሚወርድ ውሃ፣ ጠፈጠፍ። 2. የውሃ መሄጃ ቦይ። 3. ሹሩባ በተሰራ ፀጉር፣ በሹሩባዎቹ መካከል ያለው ክፍት ቦታ። 4. (ብዙውን ጊዜ ለመንግስት) ተመላሽ የሚሆን ገንዘብ።

ፈሳሽ ስ እንደ ውሃ ወይም ዘይት ያለና በቀላሉ መፍሰስ የሚችል ጠጣር ወይም ጋዝ ያልሆነ ነገር።

ፍሳሽ ስ 1. ቀዳዳ ከሆነና ከሚያፈስ ጣሪያ ላይ የሚወርድ የዝናብ ውሃ። 2. እጣቢ፣ የቆሸሸ ውሃ ወይም ጎርፍ።

ተፋሰሰ ግ 1. እየፈሰሰ ባከነ፣ ተበታተነ። 2. ወጪ ገቢን ተሳሰበ።

ተፋሰስ ስ በስተውጭ በኩል በቤት ጣሪያ ዙሪያ ለዝናብ መከላከያ ተብሎ የሚሰራ ታዛ።

አፈሰሰ ግ 1. ደፋ፣ ከነበለ፣ በተነ። 2. ሽንቁር ወይም ቀዳዳ ስለአለው ሊይዝ አለ፣ አንጠባጠበ። 3. ስልጣን ክህነቱን አፈረሰ። 4. ክብር፣ ሰውነቱ ቀንሰ፣ ያልበባ ሆነ። *ሙክቱ ላፍሰሰል።* 5. እንጀራ ጋገረ፣ አሰፋ። 6. ተናገረ፣ ገለፀ (ንዝቢን)። 7. ዘርን ከሰውነቱ (ከብልቱ) አስወጣ፣ አስወገደ (ወንድ)።8. በብዛት አወጣ (ገንዘብን፣...)።

አፋሰሰ ግ 1. እያፈሰሰ አባከነ፣ በታተነ። 2. ወጪ ገቢን አሳሳ፣ ሂሳብ አስተሳሰበ።

ፈሰከ(ፈሰገ) ግ *ፆሙን ፈታ፣ ገደፈ።*

ፋሲካ (ፋሲጋ) ስ 1. ሃምሳ አምስት ቀናት የሚፈጀው የሁዳዴ ፆም አብቅቶ ፆሙ የሚፈታበትና በአሉ የሚከበርበት እለተ እሁድ፣ ትንሳኤ። 2. ለተወሰኑ ቀናት ከተፆመ በኋላ ፍቺ የሚደረግበት ቀን፣ ፍስክ። 3. (ዘይ.) ደስታ። *ቤታቸው ሁልጊዜ ፋሲካ ነው።*

ፍስክ (ፍስግ) ስ 1. ለተወሰኑ ቀናት ከተፆመ በኋላ ፆሙ አብቅቶ ፍቺ የሚደረግበት ቀን። 2. ስጋ፣ ቅቤ፣ እንቁላል፣... የሚበላበት ወይም የማይፆምበት ጊዜ።

የፍስክ (የፍስግ) ቅ በፍስክ ጊዜ የሚበላ (ለምሳሌ ስጋ፣ ቅቤ፣...)።

ተፈሰከ (ተፈሰገ) ግ *ፆም ተፈታ።*

ፈሰፈሰ ግ 1. ደጋግሞ መታ፣ ደበደበ። 2. አንድን ነገር በብዛት አደረገ። *ምግቡን፣ ስራውን፣... ፈሰፈሰው።*

ፈሳ ግ 1. በአይነ ምድር መውጫው በኩል መጥፎ ሽታ ያለው አየር ከሆዱ አስወጣ። 2. ኋሸሸ፣ ተጨማተረ፣ ተነፈሰ።

ፈሰፈስ(ፈሰፋሳ) ቅ ፈሪ፣ ቡከን።

ፈስ ስ 1. መጥፎ ሽታ ያለውና በአይነምድር መውጫ በኩል ከሆድ የሚወጣ የተቃጠለ አየር። 2. (ዘይ.) ፈሪ።

ፈሱ ቆረጥ/ዘረጥ አለ 1. (ተራ አነ.) የፈስ ድምፅ አሰማ፣ ፈሳ።

ፈሱን ቀደደ (ተራ አነ.) ፈሱን አንዛረጠ።

ፈሱን ቆረጠ /ጨረሰ (ተራ.አነ) አንድን ነገር ለማከናወን ወይም ለማግኘት በጣም ለፋ።

ፈሱን አስረጨው (ተራ አነ.) 1. በጣም አለፋው። 2.አዘረጠው፣ በሃይል ደበደበው።

ፈሱን ጠበሰ /ጨረሰ (ተራ. አነ.) መከራውን አየ፣ ተሰቃየ።

ፈሳም (በድብ) ቅ 1.ቶሎ ቶሎ የሚፈሳ። 2. (ዘይ.) ፈሪ፣ ቡከን።

ፈስንዱስ ቅ ፈሳም።

አስፈሳ ግ 1. በሃይል መታ፣ ደበደበ። 2. በጣም ከበደ(ለምሳሌ ሸክም) ።

ፈሳሽ "**ፈሰሰ**"ስር ተመ.

ፈስ "**ፈሳ**" ስር ተመ.

ፈስንዱስ ዝ.ከ.

ፈስፋሳ "**ፈሳ**" ስር "**ፈሰፈሰ**"ን ተመ.

*ፈቀረ

ፍቅር ስ 1. ከፍተኛ የሆነ የመውደድ ስሜት (ለምሳሌ የሃገር ፍቅር /የእናት ፍቅር/ መንፈሳዊ ፍቅር)። 2. በሁለት ተቃራኒ ፆታዎች መካከል ያለና በወሲብ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ የመዋደድ፣ የመሳሳብ ስሜት። 3. ወዳጅ፣ ስምም። *ለገሬና ለገሬ ፍቅር ናቸው።*

በፍቅር ወደቀ ፍቅር ያዘው።

ፍቅር አደረበት በአንድ ነገር ላይ ከፍተኛ የሆነ ፍላጎት፣ የመውደድ ስሜት ኖረው። *የመስራት ፍቅር አደረበት።*

ፍቅር ያዘው ከተቃራኒ ፆታ ጋር በወሲባዊ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ የመውደድ ስሜት አደረበት።

የፍቅር ደብዳቤ ስ ለፍቅረኛ የሚፃፍ ደብዳቤ።

ፍቅረ ንዋይ ስ የገንዘብ መውደድ።

ፍቅሩ ጠና ስ የጥጥ ፍንድ የሚያካክል ጠጎጎታማ አበባ ያለውና በነካው ነገር ላይ ሁሉ የሚጣበቅ፣ መጠኑ አስተናግር የሚያክል የእፅዋት አይነት።

ፍቅረኛ ስ ከወሲባዊ ፍላጎት ጋር በተያያዘ ሁኔታ የሚወዱት ወይም የሚያፈቅሩት ሰው፣ ወዳጅ።

ተፈቀረ ግ ተወደደ ።

ተፈቃቀረ ግ ተዋደደ፣ ተስማማ።

ተፋቀረ ግ ተዋደደ፣ ተግባባ።

አፈቀረ ግ 1. ፍቅረኛ አደረገ። 2. ወደደ።

አፍቃሪ ቅ የሚያፈቅር፣ የሚወድ።

አፈቃቀረ ግ አፋቀረ፣ እንዲዋደዱ አደረገ።

አፋቀረ ዝ.ከ.

ፈቀቅ (ፈቅ)

ፈቀቅ አለ ግ ራቅ፣ ገሸሽ፣ ገለል አለ።

ፈቀቅ አይልም አይሄድም፣ እልፍ አይልም፣ አይንቀሳቀስም።

ፈቀቅ አደረገ ግ አራቀ፣ ገለል፣ ገሸሽ አደረገ፣ ገፋ።

ፈቀደ ግ 1. ፈቃድ ሰጠ። 2. ወደደ፣ ፈለገ፣ ከጀለ። 3. ቆጠረ፣ አስተዋለ፣ ተከታተለ። *ከብቶቹን ፍቀዳቸው* 4. ተመለከተ፣ በአይኑ ፈለገ። *ከሰው መካከል ብፈቅደው ላጣሁት።* 5. ጠበቀ፣ ጥንቃቄ አደረገ። *ህፃኑን ፍቀደው።*

በዘፈቀደ እንዳሻው፣ እንደፈለገው፣ እንደፈቀደው።

እንደፈቀደው እንዳሻው፣ እንደፈለገው።

ፈቃድ(ፍቃድ) ስ 1. አንድ ነገር ለማድረግ፣ ለማከናወን የሚመለከተው ክፍል መስማማቱን ገልፆ ጉዳዩን ለሚያከናውነው አካል የሚሰጠው ማስረጃ። *የንግድ ፈቃድ/ መንጃ ፈቃድ።* 2. ለተወሰነ ጊዜ ከስራ ነፃ መሆን እንዲቻል የሚሰጥ እረፍት። 3. ፍላጎት፣ ስምምነት። *ያለ እሱ ፈቃድ የሚሆን ነገር የለም።*

ፈቃድ ሰጠ 1. አንድ ነገር ማድረግ እንዲቻል ፈቀደ፣ ተስማማ። 2. ለተወሰነ ጊዜ ከስራው ላይ እንዲቀር ፈቀደ፣ ተስማማ።

ፍቃድ ወሰደ ለማረፍ ወይም ሌላ ጉዳይ ለማከናወን ፈቃድ ጠይቆ ከስራ ገበታው ላይ ቀረ።

የፈቃድ ወረቀት ስ አንድ ነገር ለማድረግ ወይም ለማከናወን መፈቀዱን የሚገልፅ የፅሁፍ ማስረጃ።

ፈቃድ ፈፃሚ ቅ እሺ ባይ፣ ታዛዥ።

ፈቃደኛ ቅ ግዳጅ ሳይኖርበት በራሱ ፍላጎትና ስምምነት አንድ ነገር ለማድረግ የተነሳሳ ወይም የተዘጋጀ።

ፈቃጅ ቅ ጠባቂ። *ህፃኑ ፈቃጅ የለውም።*

ተፈቀደ ግ እንዳይደረግ ተከልክሎ ወይም ታግዶ የነበረው ነገር መከልከሉ ቀረ፤ ፈቃድ ተሰጠ።

ተፈቃቀደ ግ ተጠያየቀ፣ ተባሰበ።

ተፈቃቀዱ ለፍቅር፣ ለጋብቻ፣... ተፈላለጉ። *እገሊትና እገሌ ተፈቃቅደዋል።*

አስፈቀደ ግ 1. ፈቃድ ጠየቀ። *አለቃህን አስፈቅድ።* 2. ፈቃድ አገኘ። *ከስራ የቀረው አስፈቅዶ ነው።*

ፈቀፈቀ ግ 1. ፋቀ፣ ላገ። 2. የተጣበቀ፣ የተላከከ ነገርን ለማላቀቅ ፈገፈገ።

ፍቅፋቂ ቅ 1. እንጨት ወይም ሌላ ነገር ሲፋቅ የሚወጣው ድቃቂ ወይም ገለባ። 2. ከምጣድ ላይ እልነባ ያለ የትኩስ እንጀራ ስብርባሪ።

***ፈቀፈቀ**

ፈቅፈቅ አለ እየተቀቀለ ያለ ነገር በመጠኑ ፈላ፣ ፈለቅለቅ አለ።

ፈቅፈቅ አደረገ ግ እየተቀቀለ ያለ ነገርን በመጠኑ አፈላ፣ ፈለቅለቅ አደረገ።

ተንፈቀፈቀ ግ 1. ፈላ፣ ተፍለቀለቀ (እየተቀቀለ ያለ ነገር)። 2. (ዘይ.) ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ። 3. በተከታታይ ተተኮሰ (ለምሳሌ መትረየስ)።

አንፈቀፈቀ ግ 1. አፈላ፣ አፍለቀለቀ። (እየተቀቀለ ያለ ነገርን)። 2. ስቅስቅ አድርጎ አስለቀሰ። 3. በብዛትና በተከታታይ ተኮሰ። *መትረየሱን ላንፈቀፈቀው።*

ፈቃ ግ ሰውነትን በስለት በጣ፣ ሰነጠቀ።

ፈቃደኛ "ፈቀደ" ስር ተመ.

ፈቃድ ዝ.ከ. **ፈቃጅ** ዝ.ከ.

ፈቅ "ፈቀቅ" ን ተመ.

ፈተለ^1 ግ 1. ጥጥ አባዝቶ ወይም ፈልቅቆ በእንዝርት እያከረረ ፈትል እንዲሆን አደረገ። 2. ገመደ፣ ሸረበ።

ፈታይ ቅ ጥሩ የመፍተል ችሎታ ያላት (ሴት)።

ፈትል ስ ጥጡ ተባዝቶ በእንዝርት እየተከረረ የሚዘጋጅ ማግ፣ ክር፣ ድር።

አፋተለ ግ 1. እጆቹን ወይም እግሮቹን እርስ በርሳቸው አሸ፣ አፍተለተለ። 2. እርስ በርሱ አንዱን ከሌላው ጋር አጋመደ፣ አጣመረ።

ፈተለ^2 ግ ተረበ፣ አሽሟጠጠ።

ፈታላ ቅ ተረበኛ፣ አሽሟጣጭ።

***ፈተለተለ**

ፍትልትል (ፈተልታላ) ቅ ቅልጥፍና የሌለው፣ ጎታታ (በአካሄድ፣ በስራ)።

ፍትልትል አለ ግ ተፍተለተለ።

ፍትልትል አደረገ ግ አፍተለተለ።

ተፍተለተለ ግ 1. ሲታሽ እየተድቦለቦለ ወይም እየተጥመለመለ ወጣ፣ ተነሳ (ለምሳሌ የሰውነት እድፍ)። 2. ተጎተተ፣ አልፈጥን አለ (በአካሄድ፣ በስራ)።

አፍተለተለ ግ 1. እያሸ የሰውነት እድፍን እንዲወጣ አደረገ:: 2. እንዲጎተት፥ እንዳይፈጥን አደረገ:: 3. ሆድን ቆረጠ፣ አመመ::

***ፈተለከ**

ፈትለክ አለ ግ 1. በድንገት ወይም በፍጥነት ሮጠ፣ አመለጠ:: 2. ከአንድ ነገር ውስጥ የነበረ ነገር በድንገት ወጣ::

ፍትልክ አለ ግ 1. ከታሰረ ወይም ከተጠላለፈ ክር፥ ገመድ፥... ላይ አንዱ ክፍል ላልቶ ወይም ተፈትቶ ወይም ሾልኮ ወጣ:: 2. ፈትለክ አለ::

ተፈተለከ ግ በድንገት ወይም በፍጥነት ሮጠ፥ አመለጠ::

አፈተለከ ግ 1. በድንገት ወይም በፍጥነት ሮጠ፣ አመለጠ 2. በድንገት አመለጠ:: (ከእጅ፥ ከአፍ፣...) :: 3. ከታሰረ ወይም ከተጠላለፈ ክር፥ ገመድ፥... ላይ አንዱ ክፍል ላልቶ ወይም ተፈትቶ ወይም ሾልኮ ወጣ::

ፈተልታላ"*ፈተለተለ" ስር "**ፍትልትል**"ን ተመ.

ፈተሸ ግ 1. ፈለገ፥ መረመረ፣ ጎረጎረ (የጠፋ እቃን ለማግኘት):: 2. የተደበቀ ወይም ህጋዊ ያልሆነ ነገርን ፈልጎ ለማግኘት በረበረ::3. ጉልበትን፣ ጥንካሬን ወይም አንድ ነገር መስራት አለመስራቱን ሞከረ::

ፈታሽ ስ በፍተሻ ስራ የተሰማራ ሰው::

ፍተሻ ስ 1. ህጋዊ ባልሆነ መንገድ የሚወጡና የሚገቡ እቃዎችን፣ ሰዎችን፥... በአንድ በተወሰነ ቦታ ላይ ሆኖ የመቆጣጠር ስራ:: 2. ኪሳ::

ፈተተ ግ ቆረሰ፥ ገመሰ (ሁበስትን፥ ዛቲን)::

ተፋተተ ግ እየቆረሰ ወይም እየገመሰ ተከፋፈለ::

አፋተተ ግ እየቆረሰ ወይም እየገመሰ አካፈለ::

ፈተነ ግ 1. ጠየቀ፣ ፈተና ሰጠ:: 2. ሞከረ፣ ፈተሸ:: 3. መረመረ:: *ወርቅ በእሳት ይፈተናል::*

ፈተና ስ 1. አንድ ሰው ስለአንድ የተወሰነ ነገር ማወቅ አለማወቁን ለመገንዘብ በፅሁፍ፥ በቃል ወይም በተግባር እንዲያሳይ የሚቀርብ ጥያቄ:: 2. ችግር፥ መከራ፣ ስቃይ::*ያልታሰበ ፈተና ገጠመው::*

ፈተና ወሰደ ስለአንድ የተወሰነ ነገር ማወቅ አለማወቁን በፅሁፍ፥ በቃል ወይም በተግባር እንዲያሳይ ተደረገ::

ፈተናውን ደፈነ የተሰጠውን የፈተና ጥያቄ ሙሉ በሙሉ መለሰ::

የፈተና ወረቀት ስ ለፈተና ተብሎ የተዘጋጀ ጥያቄ የተፃፈበት ወረቀት::

ፈታኝ ቅ 1. በጣም አስቸጋሪ፥ አድካሚ፣ የሞት ሽረት ትግል ያለበት(ሁኔታ፣ ወቅት፣...): *ፈታኝ ወቅት ላይ ነኝ::* 2. የፈተና ጥያቄዎችን ለተፈታኝ የሚያቀርብ ወይም በፈተናው ወቅት ተፈታኞችን የሚቆጣጠር (ሰው)::

ፍቱን ቅ ፈዋሽነቱ ተሞክሮ የተረጋገጠ፥ የታወቀ::*ፍቱን መድሃኒት::*

ተፈተነ ግ የችግር፥ የመከራ፣ የስቃይ ጊዜ አሳለፈ::

የተፈተነ ቅ ተመርምሮ፣ ተፈትሾ ጥራቱ ወይም ብቃቱ የታየ::

ተፈታኝ ቅ 1.ስለአንድ የተወሰነ ነገር ማወቅ አለማወቁን ለማረጋገጥ በፅሁፍ፣ በቃል ወይም በተግባር ሊጠየቅ የቀረበ (ሰው)::

ተፈታተነ ግ 1. ታገለ፣ ተከታተለ (በነገር፥ በተንኮል):: 2. አጓጓ፥ አማረ፥ አሰኘ (ለማባባት፥ ችግር ላይ ለመጣል)::

ተፈታታኝ ቅ በክፉ ነገር የሚከታተል:: 2. የሚያጓጓ፥ የሚያሰኝ (ስህተት ውስጥ ለማስገባት)::

ፈተገ ግ 1. ገብስን፥ ስንዴን፥... በውሃ እያራሰ ገለፈቱ እንዲለቅ ወቀጠ፥ ሸከሸከ:: 2. በሃይል አሸ:: 3. ቆዳን አለፋ፥ ዠለጠ:: 4. ፈገፈገ፥ ላጠ:: *እግሬን ድንጋይ ፈተገኝ::* 5. ራበ ሞረሞረ::*ረሃብ ፈተገኝ::*

ፍትግ ቅ ተወቅጦ ገለፈቱ የለቀቀ (ገብስ፥ ስንዴ፥...)::

ተፈታተገ ግ ተመሳሰለ፥ ተገጣጠበ (ሰውነት)::

ተፋተገ ግ 1. ተላፋ፥ ታገለ:: 2. ተፈጋፈገ፥ ተሻሸ:: 3. (ዘይ.)ተፋጨ፥ ተከራከረ (በተለያየ ሃሳብ፣ አመለካከት)::

አፋተገ ግ 1. አላፋ፣ አታገለ:: 2. አፈጋፈገ፥ አስተሻሸ:: 3. አፋጨ፥ አከራከረ::

ፈተፈተ ግ 1. እንጀራን ወይም ዳቦን፥... ወጥ፣ መረቅ፥...ውስጥ ቆራርሶ በመጨመር ፈረፈረ:: 2. (ዘይ.) በማያገባው ጉዳይ ገብቶ ነገር አቦካ:: 3. የመነዝነዝ ወይም የመጠዝጠዝ አይነት ህመም ተሰማ::

ፈትፍቶ አጎረሰ ጥሩ፥ አመቺ አድርጎ ወይም አሳምሮ ሰጠ፣ አቀረበ (ለምሳሌ ትምህርትን)::

ፈትፋች ቅ በሰው ጉዳይ ውስጥ ገብቶ ቀና ያልሆነ ሃሳብ የሚሰጥ፥ ነገረኛ፣ ወስዋሳ::

ፍትፍት ስ 1. እንጀራን ቆራርሶ በስጋ መረቅ ወይም ማባያ ሊሆን በሚችልና ፈሳሽነት ባለው ሌላ ነገር ውስጥ ጨምሮ በመለወስ የሚዘጋጅ ምግብ::2. (ዘይ.) ቀላል፣ የማያስቸግር::

ክፍትፍቱ ፊቱ አቀባበልና ፈገግታ ከማንኛውም ስጦታ ወይም ግብዣ ይበልጣል

ለማለት የሚነገር አባባል።

ፈታ ግ 1. የታሰረ፥ የተቋጠረ፥ የተያያዘን ነገር ኣላቀቀ፥ ኣለያየ።2. የታሰረበትን ኣወለቀ፥ በጠሰ። *ውሻው ፈትቶ ጠፋ*። 3. ትዳሩን ኣፈረሰ፤ ከሚስቱ ተለያየ። 4. ከእስር ቤት አስወጣ፥ ነፃ ለቀቀ። 5. አጠፋ፥ አፈረሰ፥ አወከ፤ በተነ።*ኣገር ፈታ*። 6. ኣሸነፈ፥ ድል ኣደረገ። *ጦር ከፈታው ወሬ የፈታው ይበልጣል*። 7. ለሞተ ሰው የፍታት ፀሎት ኣደረገ። 8. የገዘተውን ተወ፥ ሻረ፥ ግዝቱን አነሳ።9. ገደፈ።*ፆም ፈታ*። 10. ተረጎመ፥ ገለጠ፥ ኣብራራ፥ ፍቺ ሰጠ። 11. ኣቃለለ፥ መፍትሄ ሰጠ።*ችግሩን በቀላሉ ፈታው*።

መፍትሄ ስ የችግር ማቃለያ፥ ማስወገጃ ዘዴ ወይም መንገድ።

ፈት ቅ አግብታ የፈታች (ሴት)።

ፍታት ስ ለሞተ ሰው የሚፀለይ ፀሎት።

ፍቺ ስ 1. የትዳር ወይም የጋብቻ መፍረስ፥ መፋታት። 2. ትርጉም።

ፈታ አለ ግ ቀልጠፍ፥ ፈጠን፥ ዘና አለ (ለንግግር፥ ለስራ)።

ተፈታ ግ 1. የታሰረው፥ የተቋጠረው፥ የተያያዘው ተላቀቀ፥ ተለያየ። 2. ፆሙ ኣብቅቶ ፍስክ ሆነ። 3. የተሰበሰበው ተበተነ።*ገበያው ተፈታ*።

ተፈታታ ግ ተላቀቀ፥ ተለያየ (የተቋጠረው፤ የተያያዘው)።

ተፋታ ግ ከሚስቱ ተለያየ፥ ትዳሩን ኣፈረሰ።

ተፍታታ ግ 1. ተቆጣጥሮ ወይም ተተብትቦ የነበረ ነገር ተነጣጠለ፥ ተለያየ። 2. እስርስር ብሎ የነበረው ሰውነት ዘና አለ፥ ተዝናና።3. ተብራራ(ሃሳብ)።

አፈታ ግ በብዛት ወረደ፥ ፈሰሰ (ደም)።*ደም ኣፈታች*።

አፋታ ግ ባልና ሚስትን ኣለያየ።

አፍታታ ግ 1. ተቆጣጥሮ ወይም ተተብትቦ የነበረን ነገር ኣነጣጠለ፥ ኣለያየ።2. እስርስር ብሎ የነበረውን ዘና ኣደረገ፥ ኣዝናና (ሰውነትን በስፖርት)። 3. አብራራ (ሃሳብን)።

ፈታላ "**ፈተለ**^{2}" ስር ተመ.

ፈታሽ " **ፈተሸ**" ስር ተመ.

ፈታኝ "**ፈተነ**" ስር ተመ.

ፈታይ "**ፈተለ**^{1}" ስር ተመ.

ፈት " **ፈታ**" ስር ተመ.

ፈትል " **ፈተለ**^{1}" ስር ተመ.

ፈትፋች " **ፈተፈተ**" ስር ተመ.

ፈቻል ስ የተጣበቀ ወይም የተቸነከረ ነገርን ለመንቀል የሚያገለግል መንቀያ፥ ጉጠት።

ፈነቀለ ግ 1. የተጣበቀ፥ የተተከለ ነገርን ከስሩ ነቀለ፥ ኣወጣ፥ ኣፈለሰ። 2. ከፍተኛ የሆነ የሳቅ፥ የደስታ፥ የለቅሶ፥... ስሜት ከውስጥ ኣሸንፎ ወጣ።*ሳቅ ፈነቀለው*። 3. ኣፈናቀለ።

መፈንቅለ መንግስት ስ የአንድ ኣገር ህገመንግስት ከሚፈቅደው ውጪ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች በኣመፅ የሚያካሂዱት መንግስትን የመቀየር ተግባር፤ መንግስት ግልበጣ፤ ኩዴታ።

ተፈነቀለ ግ ፈለሰ፤ ወጣ፤ ተነቀለ።

ተፈናቀለ ግ ከመኖሪያ ቦታው ለቅቆ ወደ ሌላ ቦታ ለመኖር ሄደ (በጦርነት፥ በድርቅ፥... ምክንያት)።

ተፈናቃይ ቅ ከመኖሪያ ቦታው ለቅቆ ወደ ሌላ ቦታ ለመኖር የሄደ(በጦርነት፥ በድርቅ፥... የተነሳ)።

አፈናቀለ ግ ከመኖሪያው፥ ከስራው፥ ከትዳሩ ኣባረረ፤ ኣስወገደ።

ፈነቸረ ግ 1. ገደለ። 2. ጣለ፥ ዘረረ።

ተፈነቸረ ግ 1. ወደቀ። 2. ሞተ።

ፈነከረ ግ በጣም ከፈተ፤ በለቀጠ፤ ወዲያና ወዲህ ዘረጋ (ለምሳሌ ጭንና ጭንን)

ፈንካራ ቅ (ስድብ) ጉያዋን የማትከልል፤ ጭኗን ከፍታ የምትቀመጥ።

ፈነከተ ግ 1. ጭንቅላትን ተረከከ፥ መታ። 2. ከፈለ፥ ገመሰ። 3.ፈረከሰ፤ አደቀቀ።

ፍንካች ቅ ከአንድ ነገር ላይ ተከፍሎ ወይም ተፈንክቶ የወጣ፤ ክፋይ።

ፍንክት ቅ የተገመሰ፥ የተፈነከተ፤ ስንጥቅ።

***ፈነደረ**

ፈንዳራ ቅ ቂጡ ወደ ሂላ ያፈነደደ፤ ያፈነገጠ።

ፍንድር አለ ግ ኣፈነደረ።

አፈነደረ ግ ከወደ ሂላ ወጣ አለ፥ ኣፈነገጠ (ቂጥ ወይም ሌላ ነገር)።

***ፈነደሰ**^{1}

ፈንዳሳ ቅ ድንቡሽቡሽ ያለ ወፍራም።

ፍንድስ አለ ግ ተፈነደሰ።

ተፈነደሰ ግ ተጋደመ፥ ተኛ (ብዙውን ጊዜ ወፍራም ሰው)።

***ፈነደሰ**^{2}

ፍንድስድስ አለ ግ 1. ፍርክስክስ፥ ስንጥቅጥቅ አለ (የተቀቀለ ድንች፥ ንፍሮ፥...)። 2. ብዙ ቦታ ላይ ፈነዳ (ቁስል)።

ተፈነዳደሰ ግ ዝ.ከ.

ፈነደቀ ግ ተደሰተ፥ ቦረቀ፥ ፈነጨ።

***ፈነደደ**

ፈንዳዳ ቅ (በድብ) ከወገቡ ሰበር ብሎ ቂጡ የፈነደረ።

ፍንድድ ቅ ጉንብስ።

ፈንደድ አለ ግ 1. አፈነደረ (ቂጥ)። 2. መቀመጫውን ወደ ኋላ በማፈንደር አጎነበሰ።

ፍንድድ አለ ዝ.ከ.

አፈነደደ ግ 1. አፈነደረ (ቂጥ)። 2. አጎነበሰ።

ፈነዳ ግ 1. ዱ አለ፥ ጮሀ። 2. ፈካ። *አበባው ፈነዳ።* 3. ተተረተረ፥ ተሰነጠቀ (እንስራ፥ ኳስ፥ ጎማ፥...)። 4. ፈረጠ፥ መገለ። *ቁስሉ ፈነዳ።* 5. ይፋ ወጣ፥ ተገለጠ፤ በሁሉም ቦታ ተከሰተ። *አብዮት ፈነዳ/ ተደብቆ የቆየው ምስጢር ፈነዳ።* 6. ሲቆላ ፈካ (ፈንድሻ)።

ፈንድሻ ስ ሲቆሉት የሚፈካ የማሽላ አይነት፤ አበባ ቆሎ።

ፈንጂ ስ የሚፈነዳ የጦር መሳሪያ፤ ቦምብ።

ፈንጂ ቀበረ ፈንድቶ ጉዳት እንዲያደርስ ፈንጂን መሬት ውስጥ ወይም በስውር አስቀመጠ።

ፍንዳታ ስ 1. እንደ ቦምብ፥ ድማሚት፥... ያሉ ነገሮች መፈንዳት። 2. እንደ ቦንብ፥ ድማሚት ያሉ ነገሮች ሲፈነዱ የሚያሰሙት ድምፅ ወይም ጩሀት።

ፍንድ ስ ከቅርፊቱ ተላቅቆ የሚወጣ የጥጥ ጓል።

ፈነገለ^1 ግ ገፍቶ ወይም ገፍትሮ ጣለ።

ፈንጋላ ቅ ተስተካክሉ ወይም ተደላድሉ የማይቀመጥና በቀላሉ የሚፈነገል።

ፈንግል ስ በቶሎ የሚገድል የዶሮ በሽታ።

ፍንግል አለ ግ ተፈነገለ።

ተፈነገለ ግ 1. ወደቀ፥ ክንብል አለ። 2. (ዘይ.)ሞተ።

ፈነገለ^2 ግ (ባሪያን) አፍኖ ሸጠ።

ፈንጋይ " ባርያ" ስር "ባርያ ፈንጋይ"ን ተመ.

***ፈነገጠ**

አፈነገጠ ግ 1. የነበረበትን ቦታ፥ መስመር፥... ለቀቀ። 2. ከፓርቲው፥ ከቡድኑ፥... ተለየ።

አፈንጋጭ ስ በአመለካከቱ፥ በፖለቲካ አቋሙ ከፓርቲው፥ ከቡድኑ፥ .. ተለይቶ ለብቻው የሆነ፤ ተቃዋሚ፤ አንጃ።

***ፈነጠረ**

ፈንጣራ ቅ ገለልተኛ፥ ብቸኛ፥ ከሌላው ራቅ ያለ።

ፍንጣሪ ቅ ተፈናጥሮ ወይም ተወርውሮ የወጣ የአንድ ነገር ሽራፊ። *የእሳት ፍንጣሪ።*

ፈንጠር አለ ግ ገለል አለ ወይም ራቅ አለ። *ፈንጠር ብሎ ቆሟል።*

ፍንጥርጥር አለ ግ እየተፈናጠረ ብትንትን አለ።

ተፈነጠረ ግ ተፈናጠረ።

ተፈነጣጠረ ግ ተፈናጥሮ ተበታተነ፥ ተረጨ።

ተፈናጠረ ግ 1. ዘለለ፤ እንጣጥ አለ። 2. ተወረወረ። *ድንጋዩ ተፈናጥሮ መታው/ የፈላ ዘይት ተፈናጥሮ አቃጠለኝ።*

ተስፈነጠረ ግ ተፈናጠረ።

ተስፈንጣሪ ቅ 1. ተወርዋሪ። 2. (ፖለ.) ግራ-አክራሪ።

አፈናጠረ ግ ወረወረ፥ አሽቀነጠረ።

አስፈነጠረ ዝ.ከ.

ፈነጠቀ ግ 1. ወጣ፥ አበራ (ፀሃይ)። *ፀሃይ ፈነጠቀች።* 2. ደፋ፥ አፈሰሰ (ውሃን)። *ውሃውን ፈንጥቀው።* 3. ረጨ፤ በተነ። 4. ሙሉ ከነበረው ፈሳሽ ላይ በትንሹ አፈሰሰ፤ ቡልቅ አደረገ። 5. አልፎ አልፎ ጣል ጣል አለበት (ለቀለም፥ ለጌጥ)። *ነጭ የፈነጠቀበት ቀሚስ።*

ፍንጣቂ ቅ የተፈናጠቀ ወይም የተረጨ ጠብታ።

ተፈናጠቀ ግ ተረጨ።

አፈናጠቀ ግ ረጨ፥ አርከፈከፈ።

ፈነጠዘ ግ በደስታ ቦረቀ፤ ዘለለ፤ ጨፈረ።

ፈንጠዝያ ስ ደስታ፤ ቡረቃ፤ ጭፈራ።

***ፈነጠጠ**

ተፈናጠጠ ግ በበቅሎ፥ በፈረስ፥ ... ጀርባ ላይ ወይም በብስክሌት፥ በሞተር ሳይክል ላይ ከሚጋልበው ሰው ጋር በመደረብ ከበስተኋላው ተቀመጠ።

ተፈናጣጭ ቅ በበቅሎ፥ በብስክሌት፥.. ላይ ዋናውን ጋላቢ ተጠግቶ በስተኋላው በኩል በመቀመጥ አብሮ የሚጋልብ (ሰው)።

አፈናጠጠ ግ በበቅሎ፤ በፈረስ፤... ጀርባ ላይ ወይም በብስክሌት፥ በሞተር ሳይክል ላይ የሚጋልብ ሰው በስተኋላው በኩል ሌላ ሰው ደርቦ ጫነ።

ፈነጨ ግ 1. ዘለለ፥ ቦረቀ። 2. በጣም ተደሰተ፥ ፈነደቀ።

ፈነጨበት (በንዴት፥ በቁጣ) ብዙ ተናገረው።

***ፈነፈነ**

መፈናፈኛ ቅ መንቀሳቀሻ፥ መላወሻ። *ክፍሉ መፈናፈኛ የለውም፥ ጠባብ ነው።*

ተፈናፈነ ግ ወዲያ ወዲህ አለ፥ ተንቀሳቀሰ፤

ተጠጋጋ።

አፈናፈነ ግ እንዲንቀሳቀስ፥ ወዲያ ወዲህ እንዲል አደረገ (ብዙውን ጊዜ በአገልግሎት ላይ የሚውለው በአፍራሽ ቅርፁ ነው)።*የስራው ብዛት ላላፈናፍን አለው።*

ፈንታ "ፋንታ"ን ተመ.

ፈንዜ ስ ቀጠን ብሎ ጎበጥ ያለ የጎራዴ አይነት

ፈንጻራ "*ፈነደረ" ስር ተመ.

ፈንጻሳ "*ፈነደሰ^1" ስር ተመ.

ፈንጻጻ "*ፈነደደ" ስር ተመ.

ፈንድሻ "ፈነጻ" ስር ተመ.

ፈንጂ ዝ.ክ.

ፈንጋላ "ፈነገለ^1" ስር ተመ.

ፈንጋይ "ፈነገለ^2" ስር ተመ.

ፈንግል "ፈነገለ^1" ስር ተመ.

ፈንጠዝያ "ፈነጠዘ" ስር ተመ.

ፈንጣራ "*ፈነጠረ" ስር ተመ.

ፈንጣጣ ስ በሰውነት ላይ እንደ እከክ ሆኖ የሚወጣና ጠባሳ የሚተው ተላላፊ በሽታ።

ፈከረ "ፎከረ"ን ተመ.

ፈካ ግ 1. እንደ ፈንድሻ ያለ እህል ሲቆላ እንደ አበባ ፈነዳ። 2. አበበ፥ ፈነዳ(አበባ)። 3. በፊቱ ላይ ደስታ ታዬ፥ ፈገግ አለ። *ፊቱ ፈካ* ።

ፈካ አለ ግ በፊቱ ላይ ደስታ ታየ፥ ፈገግ አለ።

ፈካ ያለ ብሩህ የሆነ ወይም ያልደመቀ። *ፈካ ያለ ሰማያዊ (ቀለም)* ።

ፈወሰ ግ አዳነ፥ አሻረ።

ፈዋሽ ቅ 1. አዳኝ። *ሊያሰኝ ፈዋሽ ነው* ። 2. ፈውስ የሚሰጥ፥ የሚያድን።

ፈውስ ስ ከበሽታ መዳን፥ ደህንነት።

ተፈወሰ ግ ዳነ፥ ፈውስ አገኘ።

ፈዘዘ ግ 1. ድምቀት አጣ፥ ደበዘዘ (ቀለም)። 2. ሃይሉን ቀነሰ፥ ደበዘዘ። 3. ነቃ አልል አለ፥ ናበዘ፥ ቦዘ።

ፈዛዛ (ፍዝ) ቅ 1. ደማቅ ያልሆነ፥ ደብዛዛ (ቀለም)። 2. ነቃ ነቃ የማይል፥ ናባዛ።

አፈዘዘ ግ 1. አደነዘዘ፥ አነሆለለ። *በመድሃኒት አፈዘዘው*። 2. በጣም አስደነቀ፥ አስገረመ፥ ስሜትን ማረከ።

አፍዝ አደንግዝ ስ ያፈዛል ወይም ያነሆልላል ተብሎ የሚታመንበት የአስማት አይነት ወይም መተት።

ፈየደ ግ ጠቀመ፥ ረባ።

ፋይዳ ስ ጥቅም፥ እርባና።

ፈደፈደ ግ ያዘ፥ አስቃየ (ረሃብ፥ ብርድ)።

ፈጀ^1 ግ አቃጠለ፥ ለበለበ።

ተፋጀ ግ አቃጠለ፥ ለበለበ።

ፈጀ^2 ግ 1. ጨረሰ፥ ፈጽሞ አጠፋ። *አዲሱ በሽታ ሰውን ሁሉ ፈጀ*። 2. ያዘ፥ ቻለ። *እንስራው ሃያ ሊትር ውሃ ይፈጃል*። 3. አወጣ፥ ወሰደ። *ሹራቡ 100 ብር ፈጅቷል*።

ፍጅት ስ 1. እርስ በርስ መጫረስ፥ መተላለቅ። 2. ጭቅጭቅ፥ ውዝግብ።

ፍጆታ ስ 1. በተወሰነ ጊዜ የሚያልቀው ወይም ጥቅም ላይ የሚውለው መጠን። 2. የንግግር ተራ ወይም ፋንታ።

ተፋጀ ግ 1. ተጫረሰ፥ ተላለቀ፥ ተጋደለ። 2. ተወቃወቀ፥ ተነታረከ።

አፋጀ ግ 1. አወቃወቀ፥ አነታረከ። 2. አጋደለ፥ አጨራረሰ።

ፈገመ ግ 1. ወደቀ፥ ተደፋ። 2. ሞተ።

ፍግም አለ ግ 1. በግንባሩ ወይም በፍጢሙ ወደቀ፥ ድፍት አለ። 2. ሞተ።

*ፈገመገመ

ፍግምግም ቅ ሲሄድ የሚንገዳገድ።

ተፍገመገመ ግ ተውተረተረ፥ ተንገዳገደ።

አፍገመገመ ግ አውተረተረ፥ አንገዳገደ።

ፈገረ "ፎገረ"ን ተመ

ፈገገ ግ ፈካ፥ በራ።

ፈገግታ ስ ሳቅ በማለት በፊት ላይ የሚታይ የደስታ ስሜት።

ፈገግ አለ ግ 1. ሳቅ በማለት ደስታውን፥ አድናቆቱን፥... ገለፀ። 2. ጥቁረቱ ቀነሰ፥ ቀላ አለ (ለቆዳ ቀለም)። 3. ነጣ ወይም ፈካ አለ (ቀለም ወይም የቆሸሸ ልብስ ሲታጠብ)።

ፍግግ ፍግግ አለ ግ ሳቅ ሳቅ አለ (ህፃን)።

ፈገፈገ ግ 1. አሸ፥ ወለወለ (ለማፅዳት)። 2. ፋቀ፥ ፈቀፈቀ።

ተፈገፈገ ግ ተላላጠ፥ ተፋቀ።

ተፈጋፈገ ግ አንድ አካል ከሌላው ጋር በሃይል ተሻሸ።

ፈጋራ ስ ፊብ፥ የኩስ መውጫ።

ፈግጠው ተወው፥ የራስህ ጉዳይ፥ እንደፈለግህ። *ፈግጠው ፈግጠው ተባባሉ*።

*ፈጠመ

ፍጥምጥም(ፍጥጥም) ስ የጋብቻ ውል ወይም ፊርማ (በተጨማሪ የቀለበትን 3ኛ ፍቺ ተመ.)።

ተፈጠመ ግ በህግ የተጠየቀውን ወይም

አድርግ የተባለውን ለመፈፀም ቃል ሰጠ፣ ግዴታ ገባ።

ተፈጣጠመ ግ ተዋዋለ ወይም ተፈራረመ (ለጋብቻ)።

አፈጣጠመ ግ አዋዋለ ወይም አፈራረመ (ለጋብቻ)።

ፈጠረ^{1} ግ 1. አስገኘ፣ ሰራ። *እግዚአብሄር በመጀመሪያ ሰማይና ምድርን ፈጠረ ።* 2.ዋሸ፣ ያልሆነ ወይም ያልተደረገ ነገር ተናገረ።*ፈጥሮ ያወራል።* 3.ወለደ።*እናቴ ከፈጠረችኝ ጀምሮ እንደዚህ ዓይነት ነገር አላየሁም።* 4.አደረገ፣ ሰራ።*ምን ፍጡር ነው የምትለኝ?*

ፈጠራ ስ 1. በምርምር፣ በሙከራ፣... የሚገኝ የእውቀት ውጤት የሆነ አዲስ ነገር። 2. ከአእምሮ በማመንጨት የሚሰራ የልብ ወለድ ወይም ስነጥበባዊ ስራ።*የፈጠራ ፅሁፍ።* 3. ውሸት። *የፈጠራ ወሬ።*

ፈጣሪ ስ እግዚአብሄር።

ፍጡር ስ በምድር ላይ የሚኖር ሰው ወይም እንስሳ።

ፍጥረት ስ 1. በምድርና በሰማይ ያለ ማንኛውም ነገር። 2. ፍጡር። 3. አፈጣጠር፣ ተፈጥሮ። 4.ልጅ። *ስንት ፍጥረቶች አሉህ ?*

እንደፍጥርጥሩ እንደፈለገ፣ እንዳሻው።

ተፈጠረ ግ 1. ያልነበረ ነገር ለመጀመሪያ ጊዜ ተሰራ። 2. ሆነ፣ መጣ፣ ተከሰተ። *በመካከላቸው ቅራኔ ተፈጠረ።*

ተፈጥሮ ስ 1. የአንድ ነገር መለያ፣ ባህርይ፣ ጠባይ፣ ሁኔታ፣ አሰራር፣ አፈጣጠር። 2. እንደ ተራራ፣ ወንዝ፣... ያለ ሰው ሰራሽ ያልሆነ ነገር።*ተፈጥሮን ማድነቅ ይወዳል።*

የተፈጥሮ ቅ ሰው ሰራሽ በሆነ መንገድ ያልተገኘ፣ ያልተሰራ፣ ያልተፈጠረ።

የተፈጥሮ ሃብት ስ በተፈጥሮ የሚገኝና በጥቅም ላይ የሚውል እንደ ውሃ፣ ማእድን፣ ነዳጅ፣... የመሳሰለው ነገር።

የተፈጥሮ ህግ ስ በአለም ላይ ያለ ማንኛውም ነገር በተፈጥሮ ባህርዩ የሚያከናውነውና እያንዳንዱ የሚመራበት ተፈጥሮአዊ ስርአት (እንደመብላት፣ መጠጣት፣ መወለድ፣ መሞት፣ መምሸት፣ መንጋት፣ የወራት መለዋወጥ፣...ያለ)።

አፈጣጠር የ "**ተፈጥሮ**"ን 1ኛ ፍቺ ተመ..

ፈጠረ^{2} ግ በእግር ኳስ አጨዋወት ላይ ኳስን ወዲያ ወዲህ እያንከባለለ አታለለ።

ፈጠራ ስ በእግር ኳስ ጨዋታ ላይ ኳስን ይዞ ለማለፍ ወይም ላለመነጠቅ ወዲያና ወዲህ በማንከባለል እያታለሉ የመጫወት ዘዴ ወይም ቴክኒክ።

ፈጠረቀ ግ 1. አንድን ነገር አንቆ፣ አጥብቆ፣ ጨምቆ ያዘ። 2. አፈነዳ፣ አፈረጠ። 3. ፈነከተ፣ ተረተረ። *ማንቁርቱን በዱላ ፈጠረቀው።* 4. በሃይል ወርውሮ ጣለ።

ፈጥርቆ ያዘ 1. አስገድዶ፣ አስጨንቆ ያዘ። 2. ሙጥኝ፣ አጣብቆ ያዘ።

ተፈጠረቀ ግ 1. ፈነዳ፣ ፈረጠ። 2. ወደቀ፣ ተፈጠፈጠ።

ፈጠራ^{1} "**ፈጠረ**^{1}" ስር ተመ.

ፈጠራ^{2} "**ፈጠረ**^{2}" ስር ተመ.

ፈጠነ ግ 1. ቸኮለ፣ ቀለጠፈ። 2. ቶሎ ሆነ።

ፈጥኖ ደራሽ ቅ 1. በችግር ጊዜ ቶሎ ለእርዳታ የሚደርስ (ሰው፣ መልእክ፣ ...)። ስ 2. ችግር በተፈጠረበት ወይም ፀጥታ በሚደፈርስበት ቦታ ሁኔታውን ለማረጋጋት ወይም ለመቆጣጠር ቶሎ በቦታው የሚገኝ ወታደራዊ ክፍል።

ፈጣን ቅ 1. ቀልጣፋ። 2. ቶሎ የሚደርስ፣ ብዙ ጊዜ የማይፈጅ።3. ቶሎ የመገንዘብ፣ የመረዳት፣... ችሎታ ያለው፣ ንቁ።

ፍጥነት ስ 1. በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ የአንድ ጉዳይ ቶሎ የመፈፀም መጠን፣ ልክ። 2. ቅልጥፍና። 3. ችኮላ፣ ጥድፊያ።

ተፋጠነ ግ በቶሎ ወይም ሳይዘገይ ተከናወነ።

አፈጠነ ግ 1. ቀለጠፈ፣ በፍጥነት፣ ሳይዘገይ፣ በቶሎ አከናወነ።2. በፍጥነት የሚከናወን አይነት ሆነ፣ ቀለለ። *ስራው አፈጠነኝ።*

አፋጠነ ግ 1. ቶሎ፣ ሳይዘገይ ወዲያውኑ አከናወነ። 2. አጣደፈ።

አፋጣኝ ቅ አስቸኳይ፣ አጣዳፊ።

ፈጠጠ ግ 1. ጎረጠ፣ ተጎለጎለ (አይን)። 2. በደንብ ወደ ውስጥ ካለመግባት፣ ካለመቀሳቀል፣ካለመብሰል፣ ... የተነሳ ወደ ውጪ ወጣ፣ ጎላ ብሎ ታየ።*የተዘራው ዘር ፈጦ ታየ /ወጡ ውስጥ ያለው ሽንኩርት ፈጦ ታየ።*

ፈጠጤ ስ 1. እህል ተዘርቶ አፈር ሳይለብስ በመቅረቱ ከላይ ሆኖ የሚታይ ዘር። 2. ፈጣጣ (ለአይን)።

ፈጣጣ ቅ አይኑ የፈጠጠ ወይም አይኑ ወጣ ወጣ ብሎ የሚታይ።

ተፋጠጠ ግ ፊት ለፊት ተገጣጠመ፣ በመፈራራት፣ በጥላቻ፣ በጠላትነት ተያዩ ።

አፈጠጠ ግ 1. ትክ ብሎ ወይም አትኩሮ ተመለከተ። 2. አይኑን ጎለጎለ፣ አጉረጠረጠ።3. ቀላመጠ፣ ከጀለ። 4. ተቆጣ፣ ጥል ፈለገ። 5. ጉልህ፣ ግልፅ ሆኖ ታየ።

አፍጣጭ ቅ ቀላዋጭ።

ያፍጣጭ ስ ለቀላዋጭ ሰው የሚሰጥ ምግብ ወይም ጉርሻ።

አፋጠጠ ግ አስጨነቀ፥ ወጥሮ ያዘ።

ፈጠፈጠ ግ 1. ፈነከተ፥ ፈረከሰ (ብዙውን ጊዜ ጭንቅላትን)። 2. ጣለ፤ አፈረጠ።

ተፈጠፈጠ ግ 1. ተፈነከተ፤ ተፈረከሰ። 2. ወደቀ፥ ፈረጠ።

ፈጣሪ "**ፈጠረ**¹" ስር ተመ.

ፈጣን "**ፈጠነ**" ስር ተመ.

ፈጣጣ "**ፈጠጠ**" ስር ተመ.

ፈጨ ግ 1. አደቀቀ፤ ሰለቀ። 2. ጨፈለቀ፥ ጸጠ። 3. አብዝቶ አደረገ፥ ፈፀመ፤ ... ። *ወሬውን ሲፈጭ አመሸ/ያን ሁሉ መንገድ በእግሩ ፈጨሁት።*

ወፍጮ ስ በፊደል ተራው ተመ.

ፈጪ (ፈጫይት ፈጭታ) ስ በመፍጨት ስራ የምትተዳደር ሴት።

የፈጫይ ስ በመፍጨት ስራ ለምትተዳደር ሴት የሚከፈላት የጉልበት ዋጋ።

ፍጩ ስ የተፈጨው ዱቄት።

ተፋጨ ግ 1. ተፋተገ፥ ተፈጋፈገ (ለቢላዋ)። 2. ተጨቃጨቀ፥ ተከራከረ።

***ፈጨረጨረ**

ተፍጨረጨረ ግ ለፋ፤ ተጣጣረ።

ተፍጨርጫሪ ቅ ታታሪ።

አፍጨረጨረ ግ 1. እንዲጣጣር፥ እንዲፍጨረጨር አደረገ። 2. አለፋ፥ አጣጣረ።

***ፈጨጨ**

ፍጭጭ አለ ግ በጥቂቱ ወጣ፥ ፈሰሰ (ለምሳሌ መግልና እዥ)።

***ፈጨፈጨ**

ፈጨፈጭ ቅ የወረዛ ወይም ውሃ የቋጠረ (መሬት)።

ፈጭፋጫ የሚያስቀዝነው ወይም የሚያስቀምጠው።

ተንፈጨፈጨ ግ 1. ረጠበ፤ ወረዛ፥ ጨቀየ። 2.ቀዘነ። 3. እርጥብ እንጨት ሲነድ አረፋ መሳይ ነገር በማውጣት ቸስ አለ።

አንፈጨፈጨ ግ አስቀዘነ።

ፈጪ "**ፈጨ**" ስር ተመ.

ፈጫ ስ በወንዝ ወይም በጅረት ዳር የሚገኝ አሸዋ ወይም ጠጠር።

ፈጫይ "**ፈጨ**" ስር "**ፈጪ**"ን ተመ.

ፈጭታ ዝ.ክ.

ፈጭፋጫ "**ፈጨፈጨ**" ስር ተመ.

ፈፀመ ግ 1. ጨረሰ፤ አጠናቀቀ። 2. ስራ፥ አደረገ፤ አከናወነ። *ወንጀል ፈፀመ።*

ፈፅሞ ተው.ግ. ጭራሽ፥ ጨርሶ። *እቃው መኖሩን ፈፅሞ አላየሁም።*

ፍፁም ቅ 1. ፈፅሞ። 2. ምንም እንከን ወይም ጉድለት ወይም ስህተት የሌለው። 3. የበቃ፥ ፃድቅነት ደረጃ የደረሰ። *በገዳሙ ውስጥ አንድ ፍፁም ባህታዊ ነበሩ።*

በፍፁም ተው.ግ. በጭራሽ።

ፍፁም ቅጣት ምት ስ (ስፖ.) የፍፁም ቅጣት ክልል ተብሎ በተወሰነው አካባቢ ጥፋት ሲፈፀም ለተቃራኒው ቡድን የሚሰጥ የቅጣት ምት።

ፍፃሜ ስ መጨረሻ፥ ማለቂያ፥ ማከተሚያ፥ መደምደሚያ።

ተፈፀመ ግ 1.አለቀ፥ ተጠናቀቀ፥ አበቃ። 2. ተሰራ፤ ተከናወነ።

ተፈፃሚ ቅ 1. ተግባራዊ። *መመሪያው ተፈፃሚ ሊሆን አልቻለም።* 2. ተግባራዊ የሚሆን።

አስፈፀመ ግ አስጨረሰ፥ ፍፃሜ እንዲያገኝ አደረገ።

አስፈፃሚ ቅ 1. አንድ ስራ በተገቢው ሁኔታ መከሄዱን የሚከታተልና የሚቆጣጠር።ስ 2. አንድን ህግ፤ መመሪያ፤ ጉዳይ፥..., ተግባራዊ የሚያደርግ ወይም የሚያስደርግ ክፍል ወይም አካል። *ጉዳዩን ህግ አስፈፃሚው አካል ይከታተለዋል።*

አፈፃፀም ስ 1. አሰራር፥አንድን ነገር በስራ ላይ የማዋል ሂደት። 2. ተግባራዊነት። *በመመሪያው አፈፃፀም ላይ ችግር አለ።* 3. አጨራረስ።

ፈፉ ስ ጎርፍ የቦረቦረው ወይም የሸረሸረው ጉድባ፥ ገደል።

ፉ የ"**ፈ**" ፊደል ካእብ ዘር።

ፉር

ፉርቺ (ፉርፉር) ስ እንደ ቆርኪ፥ ክብ የቅል ስባሪ፥... ያሉት ሁለት ቦታ በመብሳትና ክር በቀዳዳዎቹ በማስገባት እያሽከረከሩ የሚጫወቱበት የልጆች መጫወቻ።

ፉር አለ ግ 1. በድንገትና በፍጥነት ብር ወይም ቱር አለ። 2. የጋማ ከብት በአፍንጫው አየር በማስወጣት ድምፅ አሰማ።

ፉር ፉር አለ ግ ፉርቺ ሲሽከረከር የሚያሰማውን አይነት ድምፅ አሰማ።

ፉርሽ "**ፎረሸ**" ስር ተመ.

ፉርቺ "**ፉር**" ስር ተመ.

ፉርኖ ስ በዘመናዊ የዳቦ መጋገሪያ ከፉርኖ ዱቄት የሚጋገር ነጭ ዳቦ።

ፉርኖ ዱቄት ስ ለፉርኖ የሚሆን በጣም ነጭ

የሆነ የስንዴ ዱቄት።

ፉርሽካ "ፍሩሽካ" ን ተመ.

ፉርጎ ስ ክፍት ወይም ዝግ የሆነና እንደ ጋሪ ያለ፥ ለሰው ወይም ለእቃ፥... ማጓጓዣ የሚሆን የባቡር ክፍል።

ፉርፉር "ፉር" ስር "ፉርቲ"ን ተመ.

ፉሮ ስ የሚያስነጥስ በአፍንጫ ንፍጥ የመሰለ ነገር የሚያስወጣ የጋማ ከብት በሽታ።

ፉቅራ ስ ዛር ወይም ውቃቢ ያለበት ቃልቻ።

ፉት

ፉት አለ ግ 1. በትንሹ ጠጣ፥ ቀመሰ። 2. ቶሎ ጨረሰ፤ አጠናቀቀ።

ፉት ቢሉት ጭልጥ በጣም ትንሽ ወይም ጥቂት የሆነ።

ፉት አደረገ ግ በፍጥነት ጨረሰ፥ አጠናቀቀ። *ስራውን በአንድ ጊዜ ፉት አደረገው።*

ፉንን "ፎነነ" ስር "ፎናና"ን ተመ.

ፉንጋ ቅ ፊቱ አጭርና አፍንጫው ጎራዳ የሆነ።

ፉክራ "ፎከረ" ስር ተመ.

ፉካ ስ 1. እንደ ፈሳሽ፥ ብርሃን፤ አየር፥... ያሉ ነገሮችን እንዲያስተላልፍ በግንብ ላይ አልፎ አልፎ የሚበጅ ሽንቁር፤ ቀዳዳ። 2. በተዘጋ በር ወይም ግድግዳ በኩል ለመነጋገር ወይምመልእክት ለመለዋወጥ የሚያስችል እንደመስኮት ያለ ትንሽ ቀዳዳ።

ፉክክር "ፎከረ" ስር ተመ.

ፉገራ "ፎገረ^{2}" ስር ተመ.

ፉጨት "*ፏጨ"ስር ተመ.

ፊ የ"ፈ" ፊደል ሳልስ ዘር።

ፊሊት ስ እንደ ዝንብ፥ ቢምቢ፤ ቁንጫ፥... ያሉ የቤት ውስጥ ተባዮችን ማጥፊያ መድሃኒት።

ፊሳ ስ ቀጠን ያለና የሸንበቆ ላንፋ የሚመስል፥ በወንዝ ዳር የሚበቅል የሳር አይነት።

ፊል

ፊል ፊል አለ ግ 1. ከመሬት ፍልቅ ፍልቅ እያለ ወጣ (የምንጭ ውሃ)። 2. ፈላ፥ ተፍለቀለቀ (ተጭን ወጥ)።

ፊልም ስ 1. ከሜራ ውስጥ ተደርጎ ምስል የሚቀረፅበት ስስ ፕላስቲክ መሰል ነገር። 2. "ሲኒማ" ን ተመ.

ፊልም ቤት ስ ሲኒማ ቤት።

ፊልትሮ ስ 1. የሞተርን ዘይት የሚያጣራ የመኪና እቃ። 2. አየር አጣርቶ ወደ ካርቡሬተር የሚያስተላልፍ የመኪና እቃ።

ፊር

ፊር አለ ግ ፊሽካ ሲነፋ የሚሰጠውን ድምፅ አይነት አሰማ።

ፊሽካ ስ በትንፋሽ አማካይነት እንደ ፉጨት ያለ ወይም ፊርር... የሚል ድምፅ የሚያወጣ፥ ከቆርቆሮ ወይም ከሌላ ነገር ሊሰራ የሚችል አነስተኛ እቃ (ብዙውን ጊዜ የስፖርት ዳኞችና ፖሊሶች የሚገለገሉበት)።

ፊቀን ስ እንደ ገንቦ፥ መንቀል፤ እንስራ፥... ያለ የውሃ መያዣ እቃ።

ፊተኛ "ፊት" ስር ተመ.

ፊታውራሪ ስ በቀድሞ ጊዜ በጦርነት ወቅት በፊት በኩል ያለውን ጦር ለሚመራ ወይም የፊት ጦር አዝማች ለሚሆን ሰው ይሰጥ የነበረ የማእረግ ስም።

ፊት ስ 1. ከአገጭ እስከ ግንባር መጨረሻ ያለውና አፍ፥ አፍንጫ፥ አይን፥... ያለበት የራስ ክፍል። 2.በፊት ላይ የሚታይ የመቆጣትን፥ የመደሰትን፥... ሁኔታ የሚገልፅ ስሜት። *ከፍትፍቱ ፊቱ።* 3. ቀድሞ የሚታይ፥ ከውጭ በኩል ያለ የአንድ ነገር ገፅታ ወይም አካል። *መኪናው በፊቱ በኩል ተጎድቷል።* 4. ቀድሞ፥ ጥንት፤ ድሮ፥ በፊት። *ፊት እንገናኝ ነበር አሁን ግን ተገናኝተን አናውቅም።*

ከፊቱ ይነበባል የተሰማው ስሜት ፊቱ ላይ ይታያል ወይም ያስታውቃል።

ፊቱ ሳንባ መሰለ ፊቱ ቀላ (ከብስጭት፥ ከንዴት፥ ከፀሃይ ብዛት፥... የተነሳ)።

ፊቱ ተለወጠ /ተለዋወጠ/ ልውጥውጥ አለ በንዴት፤ በድንጋጤ፤ በሃፍረት፤ በሀመም፥... የተነሳ ፊቱ ላይ የሚታየው ስሜት ተለወጠ ወይም ተቀየረ።

ፊቱ ደም መሰለ ተናደደ፤ ተቆጣ።

ፊቱን መለሰ ምህረት አወረደ፤ ይቅር አለ፥ ታረቀ (ብዙውን ጊዜ እግዚአብሄር)።

ፊቱን አይመልስም አያወላውልም፤ አያፈገፍግም፥ ውሳኔውን አይሽርም፥ ውሳኔውን አያሽርም።

ፊቱን ቋጠረ ተኮሳተረ፤ የመቆጣት ወይም የመናደድ ስሜት ፊቱ ላይ ታየበት።

ፊቱን አስመታ/ አስወጋ ወደ አንድ ቦታ ለትንሽ ጊዜ ብቅ በማለት መኖሩን አሳወቀ፥ አሳየ።

ፊቱን አዞረ ጠላ፤ ተቀየመ፥ ችላ አለ።

ፊቱን ከሰከሰ ፊቱን አኮሳተረ፤ አጠቆረ።

ፊቱን ኮሶ አስመሰለ ፊቱን ጨፈገገ፥ አኮሳተረ።

ፊቱን ከፋው የሃዘን ወይም ያለመደሰት ስሜት በፊቱ ላይ ታየ።

ፊት ሰጠ 1. ተቃለደ። 2. መቆጣትና መቆጣጠሩን ትቶ እንደ ልቡ ወይም እንዳሻው እንዲሆን አደረገ፤ አቀበጠ።3. እንዲቀርበው ወይም እንዲወዳጀው አደረገ።

ፊት ነሳ ችላ አለ፥ አላቀርብ አለ።

ፊት አሳየ ፊት ሰጠ።

ፊት ፊት አለ ቀደም ቀደም አለ።

ወደፊት ተው.ግ. 1. ለሚቀጥለው፣ ለሚመጣው ጊዜ። 2. የአንድ ድርጊት እንቅስቃሴ እንዲቀጥል ለማበረታታት ከመፈክር ጋር የሚባል። *ማይምነትን ለማጥፋት ወደፊት!* 3. በግንባር ትይዩ ወደአለው አቅጣጫ። *ወደፊት ሂድ።*

ፊት ለፊት ተው.ግ. 1. ግንባር ለግንባር፥ በአካል በመገናኘት (በአንድ ጉዳይ ላይ ለመነጋገር፣ ለመወያየት፥...)። 2. ትይዩ። *ሱቁ ከት/ቤቱ ፊት ለፊት ነው።* 3. በፊት በኩል ያለው አቅጣጫ። 4.በአሽሙር ወይም በስውር ያልሆነ፥ በግልፅ። *ፊት ለፊት ሰደበው።*

ፊት መመለሻ /መግለጫ ስ እጅ መንሻ፥ ስጦታ።

ፊት መሪ ስ በሰልፍ ጊዜ ከፊት ሆኖ የሚመራ።

ፊትና ኋላ ተው.ግ. በቅደም ተከተል፥ በመከታተል።

ፊተኛ ቅ 1. ቀድሞ የነበረ። 2. ከፊት ያለ።

ፊና ስ ወገን፥ በኩል። *ሁሉም በየፊናው ሄደ።*

ፊናንስ [ፖሊስ] ስ ህጋዊ ቀረጥ ያልተከፈለባቸው ወይም ፈቃድ የሌላቸው እቃዎች በገበያ ላይ እንዳይውሉ ወይም ከሃገር ወደሃገር እንዳይዘዋወሩ የሚቆጣጠር አካል።

ፊን

ፊን አለ ግ 1. ውሃ ወይም ሌላ ፈሳሽ ነገር ቀጠንና ረዘም ብሎ በሃይል ወጣ፥ ተረጨ። 2. (ዘይ.) ድንገት ተቆጣ፣ ተቆናጠረ።

ፊን ፊን አለ ግ ቆጣ ቆጣ አለ፥ ተቆናጠረ።

ፊንጢጣ ስ በሰውና በእንስሳት አካል ላይ የሚገኝ የአይነምድር ወይም የኩስ መውጫ።

ፊኖ^1 ስ ሲሚንቶና ደቃቅ አሸዋ ከውሃ ጋር ተደባልቆ የሚዘጋጅ የግድግዳ መለሰኛ፤ልስኑም ፊኖ ይባላል።

ፊኖ^2 **[ዱቄት]** ስ ፉርኖ ዱቄት።

ፊኛ ስ 1. ሽንት በቆሻሻነት ወደ ውጭ ከመውጣቱ በፊት በሰውነት ውስጥ የሚጠራቀምበት ከረጢት። 2. በትንፋሽ እየተነፋ እንደ ኳስ የሚለጠጥ የልጆች መጫወቻ ላስቲክ።

ፊው

ፊው አለ ግ 1. የፉጨት አይነት ድምፅ ተሰማ። 2. በድንገትና በፍጥነት ሽው አለ፥ ቱር አለ።

ፊውዳሊዝም ስ ከባሪያ አሳዳሪው ስርአተ ማህበር ቀጥሎ የመጣ ገበሬውና የመሬት ከበርቴው ዋነኛ መደቦች ሆነው የሚገኙበት ስርአተ ማህበር።

ፊውዳል ስ 1. በፊውዳሊዝም ስርአተ ማህበር የመሬት ባለቤት የሆነና ስልጣን ያለው የገዢ መደብ። ቅ 2. የፊውዳል ስርአተ ማህበር አመለካከትን የያዘ ወይም የሚያንፀባርቅ።

ፊደል ስ ንግግርን በፅሁፍ ለማስፈር የሚያስችልና ድምፅን ወክሎ የሚቆም ምልክት (ለምሳሌ ሀ፥ለ፥...)።

ፊደል ቆጠረ / ለየ ፊደሎችን (ፊደሳትን) ተማረ፥ ማንበብ ቻለ። *ፊደል የቆጠረው ቄስ ት/ቤት ነው።*

ፊደል አስቆጠረ/አስለየ ፊደል አስተማረ፥ አሳወቀ።

ፊደል ሃዋርያ ስ በቄስ ት/ቤት ልጆች የፊደል ትምህርት ከጨረሱ በኋላ ንባብ ማንበብ የሚለማመዱበት የዮሃንስ መልእክት አጭር ፅሁፍ።

ፊደል ተራ ስ የፊደሎች ቅደም ተከተል።

ፊደል ገበታ ስ በአንድ ቋንቋ ውስጥ ያሉ ፊደላት በሙሉ በቅደም ተከተላቸው ተመዝግበው የሚገኙበት ወረቀት ወይም ሰሌዳ።

ፊጥ

ፊጥ አለ ግ ከፍ ወይም ረዘም ያለ ነገር ላይ ወጥቶ ቁጢጥ፥ ቁጭ፥ ቁብ አለ።

ፊጥኝ ስ ሁለት እጅን ወደኋላ በማዞር የሚያስሩት አስተሳሰር።

የፊጥኝ አሰረ ግ ሁለት እጅን ወደ ኋላ በማድረግ አሰረ።

ፉ የ "ፈ" ፊደል ራብእ ዘር።

ፉልማ ቅ በወንዝ ዳርና ዳር የሚገኝ ለም የሆነ መሬት።

ፋመ ግ ፍም ሆነ።

ፍም ስ እንጨት ወይም ከሰል በእሳት ተቀጣጥሎ ነበልባሉ ከለቀ በኋላ የሚቀረውና ወደ እሳትነት ተለውጦ የሚገኘው የእንጨቱ ወይም የከሰሉ አካል።

ፍሙ ወረደ እንጨቱ ወይም ከሰሉ ነዶ ፍም ሆነ።

ተፋፋመ ግ ተሟሟቀ፥ ተጋጋለ፥ ተቧቧፈ (ጦርነት፣ ጠብ፣ ክርክር፥...)።

አፋመ ግ 1. ፍም ሆነ፥ ፍም በብዛት ወረደ። 2. ከእንጨት ወይም ከከሰል ፍም አዘጋጀ።

አፋፋመ ግ 1. አሟሟቀ፡ አጋጋለ:: 2. አጣደፈ፥ አስጨንቆ ያዘ፡ አዳረሰ::ምጡ አፋፍሟታል::

ፋረ ግ ጫረ፤ ቆፈረ (በጥፍር፥ በዶማ፥ ...)::

ፋራ ስ የሰው ወይም የከብት ዱካ::

ፋሮ ስ መሬት የሚጭር ወይም የሚቆፍርና እግሮቹ አጫጭር የሆኑ እንደ ድመት ያለ አውሬ::

ፋራ^{1} ቅ (ያራዳ አነ.) ያልሰለጠነ፡ ከርፋፋ፥ ባላገር::

ፋራ^{2} **"ፋረ"** ስር ተመ.

ፋራናይት ስ የሙቀት ወይም የቅዝቃዜ መጠን መለኪያ:: 212^{0} ፋራናይት 100^{0} ሴንቲግሬድ ይሆናል::

ፋራፋንጎ "ፈረፋንጎ"ን ተ.መ.

ፋርማሲ ስ የመድሃኒት መሸጫ መደብር::

ፋሮ "ፋረ" ስር ተመ.

ፋሲካ (ፋሲጋ) "ፈሰከ" ስር ተመ.

ፋስ ስ 1. ከስለቱ በኩል ወደ እጀታው ነጠፍ ያለና እንጨት ለመጥረብ፡ ምስማር ለመምታትና ለመንቀል የሚያገለግል የአናጺ መሳሪያ፡ 2. መጥረቢያ::

ፋስ 1ኛ ፍቺ

***ፋሸከ**

ፍሽኪያ (ፍሽጊያ) ስ ማዛጋት::

አፋሸከ (አፋሸገ) ግ አዛጋ::

ፋሻ ስ 1. ለቁስል መሸፈኛ ወይም ማሰሪያ የሚያገለግል በጥቅል ሆኖ የሚዘጋጅ ነጭና ረዥም ጨርቅ::

ፋሺስት ስ 1. አጀማመሩ በኢጣሊያ ውስጥ የሆነውን የቀኝ ክንፍ አክራሪና አምባገነናዊ አመለካከትን የያዘ የፖለቲካ መስመር ተከታይ::2. (ዘይ.) አረመኔ፡ ጨካኝ፤ ነፍሰ ገዳይ::

ፋሽን ስ በአንድ በተወሰነ ወቅትና ቦታ በህብረተሰቡ ዘንድ ቀደም ሲል ከነበሩት የበለጠ ተቀባይነት ያለው ጊዜ አመጣሽ አስተሳሰብን፥ አነጋገርን፥ ልብስን፡ አለባበስን፡ የፀጉር አሰራርን፡... የሚመለከት ሁኔታ ወይም አድራጎት::

ፋሽኑ ያለፈበት በአንድ በተወሰነ ወቅትና ቦታ በህብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ኖሮት በኋላ ግን ተቀባይነት ያጣ (የአስተሳሰብ፥ የአነጋገር፤ የልብስ፥ የአለባበስ፥ የፀጉር አሰራር፡... አይነት)::

ፋሽኮ ስ ከወገቡ በታች በሰሌን የተሸፈነና ቂጡ ላይ እንደ ማቶት ሆኖ የተሰራ ማስቀመጫ ያለው የቪኖ ጠርሙስ::

ፋሽኮ

ፋቀ^{1} ግ 1. ላጠ፡ መለጠ፡ ፈገፈገ:: 2. በመፋቂያ ጥርስን አሟጨ፥ አፀዳ:: 3. ሰረዘ፥ ደመሰሰ፡ አጠፋ (ፅሁፍን)::

መፋቂያ ስ የጥርስ ማፅጃ፡ መፋቂያ እንጨት::

ፋቂ ስ ለልዩ ልዩ አገልግሎት ሊውል የሚችል የእንስሳት ቆዳን እየፋቀና እያለፋ የሚያለሰልስ ባለሙያ::

ፋቀ^{2} ግ አቃረ::

ፋቅ ስ ቃር::

አፋቀ ግ አቃረ::

ፋቂ "ፋቀ^{1}" ስር ተመ.

ፋቅ "ፋቀ^{2}" ስር ተመ.

ፋብሪካ ስ በተለያዩ ማሽኖች የተለያዩ ቁሳቁሶች በብዛት የሚመረቱበት ድርጅት::

ፋታ ስ ጥቂት እረፍት::

ፋታ ሰጠ እንዳይቸገር፥ እንዳይጨነቅ፡ እንዳይጣደፍ፡... ጊዜ ሰጠ::

ፋነነ ግ 1. ፈረጠጠ፡ በረቀ፡ ፈነጨ:: 2. በውዴታ ወይም በገዛ ፈቃዱ ዘመተ::3. አውደለደለ፡ ባዘነ::

ፋኖ ስ ሳይታዘዝ በፈቃዱ የሚዘምት፡ ወዶ ዘማች::

ፋና ስ የጧፍ፥ የፋኖስ፡... መብራት ወይም ብርሃን::

ፋና ወጊ ስ በድሮ ጊዜ በቤተመንግስት ወይም በመኳንንት ቤት ማታ ማታ የእንጨት ወይም የጧፍ መብራት ይዞ የሚቆም አሽከር::

ፋንታ (ፈንታ) ስ 1. ድርሻ:: *ይህ ዳቦ የእኔ ፋንታ ነው::* 2.ተራ፥ ወረፋ:: *አሁን መጫወቱ የእኔ ፋንታ ነው ::* 3.ምትክ:: *በእኔ ፋንታ እሱ ይሄዳል::*

ፋንድያ ስ የጋማ ከብት ኩስ::

ፋኖ "ፋነነ" ስር ተመ.

ፋኖስ ስ ነጭ ጋዝ ተጨምሮበት መስታወት መሰል ብርጭቆ ውስጥ ያለው ክር ሲቃጠል ብርሃን ሊሰጥ የሚችል የመብራት እቃ::

ፋክቱር ስ ለተገዛ እቃ፡ ለትራንስፖርት፡... ለወጣ ወጪ ማስረጃ እንዲሆን የወጣው የገንዘብ

ፋኖስ

ልክ የተፃፈበት ወረቀት፤ ደረሰኝ ወይም ማስረጃ።

ፋይል ስ የህይወት ታሪክ ወይም የክስ ወይም የማመልከቻ፣... ደብዳቤዎችን የያዘ ማህደር፣ ክላሰር፣ ዶሴ።

ፋይል ከፈተ 1. ክስ መሰረተ። 2. አንድን ጉዳይ በተመለከተ የተፃፉና የሚፃፉ ደብዳቤዎች የራሱ መለያ ቁጥር ባለው ማህደር ውስጥ እንዲቀመጡ አደረገ።

ፋይናንስ ስ የገንዘብ ገቢና ወጪ ነክ ጉዳይ። *የአስተዳደርና ፋይናንስ አገልግሎት።*

ፋይዳ "**ፈየደ**" ስር ተመ.

***ፋደሰ**

አፋደሰ ግ አውደለደለ፤ ያለስራ ወዲያ ወዲህ አለ።

አፋዳሽ ቅ (ስድብ) አውደልዳይ።

ፋደት ስ የሚከረፋ ሽታ ያለው፤ ጅራቱ ጎፍላ የሆነና መልኩ ጥርኝ የሚመስል አውሬ (ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።

ፋገ ግ በትንሹ የነበረው እየሰፋ ሄደ (እሳት፣ ቁስል)።

አፋገ ግ ፋገ።

ፋገረ (ፏገረ) ግ 1. ለፋ፣ ወጣ ወረደ፣ ደከመ። 2. ጫረ፤ ጎደፈረ፣ ቆፈረ፤ ፎገረ።

ፋጉሎ ስ 1. ተጠምቆ ዘይቱ ከወጣ በኋላ የሚቀረው የኑግ ወይም የተልባ አሰር፤ አተላው። 2. (ዘይ፣ ስድብ) መልከ ጥፉ።

ፋጋ ስ ለጠላ መጠጫ፣ ለውሃ መጥለቂያ፣... የሚያገለግል አፈ ሰፊ እንስራ ወይም የቅል ጉማጅ።

ፋፋ ስ ከተለያዩ የእህል አይነቶች በፋብሪካ ውስጥ ተዘጋጅቶ በሳስቲን እየታሸገ ለህፃናት ምግብነት የሚቀርብ የምግብ ዱቄት።

ፋፋ ግ ወፈረ፣ ዳበረ (ህፃን፣ ተክል፣...)።

ፌ የ "ፈ" ፊደል ሃምስ ዘር።

ፌራ ስ በንክኪ የሚተላለፍ የተስቦ በሽታ።

ፌርማታ ስ የከተማ አውቶቡስ ቆሞ ተሳፋሪዎችን የሚያሳፍርበትና የሚያወርድበት ቦታ።

ፌቆ ስ በተራራና በገደል የምትኖርና ፍየል የምትመስል የዱር እንስሳ (ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።

ፌንጣ ስ አንበጣ የሚመስል፤ ሳር የሚበላና ሲሄድ ጡብ ጡብ የሚል የነፍሳት አይነት።

ፌንጣ

***ፌዘ**

ፌዝ ስ ቀልድ፤ ቧልት።

ፌዘኛ ቅ ቀልደኛ፣ቧልተኛ።

አፌዘ ግ ቀለደ፤ አሳገጠ፣ አሾፈ።

ፌጦ ስ ፍሬው ሰሊጥ የሚመስል፤ ሲበሉት የሚሰነፍጥና ብዙውን ጊዜ ለመድሃኒትነት የሚገለገሉበት የቅመም አይነት።

ፍ የ "ፈ" ፊደል ሳድስ ዘር።

ፍለጋ "**ፈለገ**" ስር "**ፈለግ**"ን ተመ.

ፍላሎት "**ፈላ**^{1}" ስር ተመ.

ፍላሽ ስ በቤት ውስጥ ወይም በቂ ብርሃን በሌለበት ቦታ ፎቶግራፍ ለማንሳት እንዲቻል ተፈላጊውን ብርሃን የሚሰጥ የካሜራ መብራት።

ፍላቂ "**ፈለቀ**" ስር ተመ.

ፍላጎት "**ፈለገ**" ስር ተመ.

ፍላጭ "**ፈለጠ**" ስር ተመ.

ፍላፃ ስ ቀስት።

ፍል^{1} "**ፈላ**^{1}" ስር ተመ.

ፍል^{2} "**ፈላ**^{2}" ስር ተመ.

ፍልሚያ " **ፈለመ**" ስር ተመ.

ፍልም ዝ.ክ.

ፍልሰታ ስ (ኢ .ኦ .ተ .ቤ.) ከነሃሴ 1 እስከ ነሃሴ 16 ቀን ድረስ ያለው የፆም ጊዜ።

ፍልስልስ "**ፈለሰ**" ስር ተመ.

ፍልስፍና "**ፈለሰፈ**" ስር ተመ.

ፍልቃቂ "**ፈለቀቀ**" ስር ተመ.

ፍልቃጭ "**ፈለቀጠ**" ስር ተመ.

ፍልቅልቅ "**ፈለቀ**" ስር ተመ.

ፍልቅቅ "**ፈለቀቀ**" ስር ተመ.

ፍልጥ "**ፈለጠ**" ስር ተመ.

ፍልፈል ስ በመሬት ውስጥ የሚኖር፤ አፈሩን ከውስጥ እየቆፈረና ወደ ውጭ እየገፋ የሚቆልል አይጥ መሰል አውሬ።

ፍልፍል "**ፈለፈለ**^{2}" ስር ተመ.

ፍሎረሰንት ስ ረጅም ዘንግ የሚመስል የአምፖል አይነት።

ፍም "**ፋመ**" ስር ተ.መ.

ፍሩሽካ (ፉርሽካ) ስ 1. ዱቄት በፋብሪካ ሲዘጋጅ የሚገኝና ለእንስሳት መኖነት የሚያገለግል ተረፈ ምርት፤ የእህል አሰር። 2. የእንጨት (የጣውላ) ፍቅፋቂ፤ ሰጋቱራ።3. (ዘይ.) የማይረባ፣ ጥራት የሌለው።

ፍረሲዮን ስ ሞተርንና ትራንስሚሲዮንን ከነምቢዮ ጋር በማገናኘትና በማለያየት

የመኪናውን ፍጥነት ለመጨመርና ለመቀነስ የሚያስችል የመኪና እቃ።

ፍሬዳ ስ የተቀለበ የእርድ ከብት ወይም ሰንጋ።

ፍሬዳ ጣለ ሰንጋ ወይም በሬ ወይም መሲና አረደ።

ፍሬጅ ስ የተለያየ መጠን ያለውና በኤሌክትሪክ ሃይል የሚሰራ፥ ምግብን ወይም ሌላ ፈሳሽ ነገርን፥ መድሃኒትን፥... አቀዝቅዞና ሳይበላሽ ለረጅም ጊዜ ጠብቆ ለማቆየት የሚያገለግል፣ እቃ፣ ማቀዝቀዣ ወይም በረዶ ቤትም ይባላል።

ፍራሽ "ፈረሰ" ስር ተመ.

ፍራሽ ስ ጥጥ፥ስፖንጅ፥ ቁርጥራጭ ጨርቅ፥... በአልጋ ልክ በተሰፋ ከረጢት መሰል ጨርቅ ውስጥ አስገብቶ በመስፋት የሚዘጋጅና በመተኛነት የሚያገለግል ድልዳል።

ፍራት (ፍራቻ) "ፈራ" ስር "ፍርሃት"ን ተመ.

ፍራንክ ስ 1. ሳንቲም። 2. ገንዘብ።

ፍራንኮ ቫሉታ ስ ከሃገር ውስጥ የውጭ ምንዛሪ ሳይጠየቅ መሳሪያዎችንና እቃዎችን በፈቃድ ወደ ሃገር ውስጥ በማስገባት የሚካሄድ ንግድ።

ፍራክሽን (ሂሳ.) ስ ክፍልፋይ ።

ፍራፍሬ "*ፈራ" ስር ተመ.

ፍሬ ዝ.ከ.

ፍሬን ስ የተሽከርካሪ እግሮች እንዲቆሙ ለማድረግ ወይም ፍጥነትን ለመቆጣጠር የሚያስችል የተሽከርካሪው አካል።

ፍሬን ለቀቀ አእምሮውን መቆጣጠር እስኪሳነው ድረስ በጣም ሰከረ።

ፍሬከርስኪ (ፍሬፈርስኪ) "*ፈራ" ስር ተመ.

ፍርሃት "ፈራ" ስር ተመ.

ፍርምርም "ፈረመረመ" ስር ተመ.

ፍርምባ ስ ከአንገት በታች በፊት እግሮች መካከል የሚገኝ የከብት አካል ክፍል ወይም ብልት።

ፍርስራሽ "ፈረሰ" ስር ተመ.

ፍርቅርቅ "*ፈረቀረቀ" ስር ተመ.

ፍርንስ "*ፈረነሰ" ስር ተመ.

ፍርንትት ስ በብልትና በጭን መካከል ያለ፥ ቆዳው ለስላሳ የሆነ የሰውነት ክፍል፤ ብሽሽት።

ፍርኩታ ስ የተቦረቦረ ዋሻ፣ ጎሬ።

ፍርክርክ "*ፈረከረከ" ስር ተመ.

ፍርክስ "ፈረከሰ" ስር ተመ.

ፍርድ "ፈረደ" ስር ተመ.

ፍርጃ ዝ.ከ.

ፍርግርግ ስ 1. እንደ ኤክስ(x) ምልክት ሆኖ ወይም በሰያፍ የሚበጅ ማገር። 2. ከብረት በተሰራና ባለመስተዋት በሆነ የብረት መዝጊያ ወይም መስኮት ላይ ከብረት ዘንጎች በተለያየ ቅርፅ የሚሰራ መከታ ወይም መከልከያ፣ ግሪል።

ፍርጥም "ፈረጠመ" ስር ተመ.

ፍርፋሪ "ፈረፈረ" ስር ተመ.

ፍርፍር ዝ.ከ.

ፍሳሽ "ፈሰሰ" ስር ተመ.

ፍስሃ ስ ደስታ።

ፍስክ (ፍሰግ) "ፈሰከ" ስር ተመ.

ፍሽኪያ (ፍሽጊያ) "ፋሸከ" ስር ተመ.

ፍቃድ "ፈቀደ" ስር "ፈቃድ"ን ተመ.

ፍቅረኛ "ፈቀረ" ስር ተመ.

ፍቅር ዝ.ከ.

ፍቅፋቂ "ፈቀፈቀ" ስር ተመ.

ፍተሻ "ፈተሸ" ስር ተመ.

ፍቱን "ፈተነ" ስር ተመ.

ፍታት "ፈታ" ስር ተመ.

ፍትህ ስ ትክክለኛ ፍርድ፥ ብያኔ፣ ውሳኔ፥ በህግ መሰረት መዳኘት።

ፍትሃብሄር ስ 1. ከወንጀል ውጪ የሆኑና ከገንዘብ፥ ከንብረት፥..., ጋር የተያያዙ ጉዳዮች የሚታዩበትና ፍርድ የሚሰጥበት ህግ። 2. የፍትሃብሄር ህግ የተፃፈበት መፅሃፍ።

ፍትሃነገስት ስ በዘመናዊ መልክ የተዘጋጁት ፍትሃብሄርና ወንጀለኛ መቅጫ መፃህፍት ከመፃፋቸው በፊት መንፈሳዊና ስጋዊ ጉዳዮችን በተመለከተ የዳኝነት ጉዳይ ይታይበት የነበረ የህግ መፅሃፍ።

ፍትሃዊ ቅ ትክክለኛ፣ ህጋዊ።

ፍትልትል "*ፈተለተለ" ስር ተመ.

ፍትወት ስ 1. ምኞት፥ ፍላጎት። 2. ፍትወተ ስጋ።

ፍትወተ ስጋ ስ የወሲብ ፍላጎት።

ፍትግ "ፈተገ" ስር ተመ.

ፍትፍት "ፈተፈተ" ስር ተመ.

ፍች "ፈታ" ስር ተመ.

ፍናቅ ስ ጉድጓድ ወይም ጉድብ የበዛበት ያልተስተካከለ ቦታ።

ፍናጃ ቅ 1. ፍናቅ። 2. የግንብ ንቃቃት፣ ብስ፣ ሽንቁር።

ፍናፍንት ስ የወንድም የሴትም የተፈጥሮ

መለያዎች ያሉት ሰው፤ ወንዳገረድ።

ፍንትው አለ ግ ግልፅ ሆነ ወይም ቀልጥ ብሎ ታየ።

ፍንካች "ፈነከተ" ስር ተመ.

ፍንክች

ፍንክች አይልም ግ 1. አይበገርም፤ አይደፈርም። 2. ንቅንቅ፤ ዝንፍ አይልም፤ የማይለወጥ፥ የፀና ነው። *ከተናገረው ፍንክች አይልም።*

ፍንዳታ "ፈነዳ" ስር ተመ.

ፍንድ ዝ.ከ.

ፍንድድ "*ፈነደደ" ስር ተመ.

ፍንጃል ስ የቡና ወይም የሻይ መጠጫ፤ ስኒ።

ፍንጣሪ "ፈነጠረ" ስር ተመ.

ፍንጣቂ "ፈነጠቀ" ስር ተመ.

ፍንጥር

የፍንጥር ስ ከብት፥ እቃ፥... ሲሸጥ ገዥና ሻጭ ገንዘብ አዋጥተው ላሻሻጧቸው ወይም ላስማሟቸው ሰዎች የሚያደርጉት የደስደስ ግብዣ።

ፍንጭ ስ 1. የወሬ ወይም የአንድ ጉዳይ ጭላንጭል ወይም ምልክት። 2. የቁስል፥ የእበጥ ቀዳዳ ወይም አፍ።

ፍንጭት ስ 1. በላይኛው ሁለት የፊት ጥርሶች መካከል ያለ ክፍተት።2. ጥርሱ ፍንጭት የሆነ ሰው።

ፍንፅቅ ዘር ስ እንደ ሏ፥ ቧ፥ ሟ፥... ያሉ የፊደላት ዘር።

ፍካሬ ኢየሱስ ስ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሃዋርያት የነገራቸውንና በስምንተኛው ሺህ የሚደረገውንና የሚሆነውን ነገር ይናገራል ተብሎ የሚታመንበት የትንቢት መፅሃፍ።

ፍዝ "ፈዘዘ" ስር **"ፈዛዛ"** ን ተመ.

ፍየል ስ የበግ ቅርፅ ያለው፥ አካሉ ከርደድ ባሉና አጫጭር በሆኑ ፀጉሮች የተሸፈነ የቤት እንስሳ (ስእሉን የቤት እንስሳ ስር ተመ.)።

ፍየለ ፈጅ ስ በደጋና በወይና ደጋ አካባቢ የሚበቅል የእፅዋት ዓይነት።

ፍየል ምላስ ቅ (ዘይ.) ለፍላፊ፥ቀባጣሪ።

ፍዳ ስ መከራ፥ ስቃይ።

ፍዳ አስቆጠረ መከራ አሳየ፤ አሰቃየ።

ፍዳውን አየ ብዙ ተሰቃየ፤ መከራ ተቀበለ።

ፍጅት "ፈጀ²" ስር ተመ.

ፍጆታ ዝ.ከ.

ፍግ ስ በበረት ውስጥ ደርቆ የተሰባበረ ወይም የደቀቀ እበት፥ ፋንድያ፥ በጠጥ።

ፍግምግም "*ፈገመገመ" ስር ተመ.

ፍጡር "ፈጠረ¹" ስር ተመ.

ፍጥምጥም "*ፈጠመ¹" ስር ተመ.

ፍጥረት "ፈጠረ¹" ስር ተመ.

ፍጥነት "ፈጠነ" ስር ተመ.

ፍጥጥም "*ፈጠመ" ስር **"ፍጥምጥም"** ን ተመ.

ፍጩ "ፈጨ" ስር ተመ.

ፍፁም "ፈፀመ" ስር ተመ.

ፍፃሜ ዝ.ከ.

ፎ የ**"ፈ"** ፊደል ሳብእ ዘር።

***ፎለፎለ**

ፎልፏላ (ፎለፎል) ቅ ተጫዋች፥ ሳቂታ።

ተንፎለፎለ ግ ተንገረቀገረቀ፤ በብዛት ፈሰሰ (ፈሳሽ)።

አንፎለፎለ ግ በብዛት አፈሰሰ፥ አንዶለዶለ፥ አንገረቀገረቀ (ፈሳሽን)።

ፎሌ ስ ለመጠጫና ለውሃ መጥለቂያ የሚያገለግል ሸክና የሚመስል ቅል።

ፎልፏላ "*ፎለፎለ" ስር ተመ.

ፎረሸ ግ ሳተ፥ ተሳሳተ፥ አበላሸ (በልጆች ጨዋታ ስርአት)።

ፎርሽ ቅ ልጆች እንደ ሰኞ ማክሰኞ፥ ጠጠር፥... ያሉ ጨዋታዎችን በሚጫወቱበት ጊዜ ስህተት የሰራውን ተጫዋች ተሳስተሃል ለማለት የሚጠቀሙበት ቃል።

ፎርሽ ሆነ 1. ተሳሳተ (በልጆች ጨዋታ)።2. ከሸፈ።

ፎረፎር ስ የሚያሳክክ ደቃቅ ብናኝን በራስ ቆዳ ላይ የሚያስከትል በሽታ፤ ብናኙም ፎረፎር ይባላል።

ፎርማሊቲ ስ አንድን ጉዳይ ለማከናወን መሟላት ያለባቸውና ስርአትና ደንብን ተከትለው የሚፈፀሙ ድርጊቶች።

ፎርማጆ ስ የደረቀ አይብ።

ፎርም ስ 1. መልክ፤ አይነት፤ ቅርፅ። *በዚህ ፎርም ይሰራ።* 2. ቅፅ። *የቅጥር ፎርም።* 3. ቁንጥ።*እገሌ ላሁኑ ፎርም ላለው።*

ፎርፌ ስ (ስፖ.) በተያዘለት ጊዜና ቦታ ለውድድር ባልቀረበ ወይም በውድድር ጊዜ ጨዋታው እንዲቋረጥ የሚያደርግ የስነ ስርአት ጉድለት በፈፀመ ወገን ላይ የሚጣልና አጥፊውን ወገን ተሸናፊ የሚያደርግ ቅጣት።

***ፎሸፎሸ**

ፎሸፏሻ ቅ ምስጢር መያዝ የማይችል፥ ወሬኛ።

ተንፎሸፎሸ ግ 1. ወሬ ነዛ። 2. በሃይል ወይም በብዛት ፈሰሰ(ፈሳሽ)።

አንፎሸፎሸ ግ በብዛት አፈሰሰ፤ ለቀቀ (ፈሳሽን)።

***ፎቀቀ^{1}**

እንፉቅቅ ስ በቂጥ እየተንፏቀቁ መሄድ።

ፎቃቃ ቅ (ስድብ) መራመድ የማይችልና በቂጡ እየተንፏቀቀ የሚሄድ።

ፎቅቅ አለ ግ 1. በቂጡ እየተንፏቀቀ ወይም እየተሳበ ሄደ። 2.ራቅ ወይም እልፍ አለ፤ ፈቀቅ አለ።

ፎቅቅ አደረገ ግ ገፋ፤ ፈቀቅ አደረገ።

ተንፏቀቀ ግ በቂጡ እየተሳበ ወይም እየተንሸራተተ ሄደ።

አንፏቀቀ ግ ፎቅቅ አደረገ።

***ፎቀቀ^{2}**

ፎቃቃ ቅ (ስድብ) አሳባቂ፤ አዋሻኪ።

አንፏቀቀ ግ አሳበቀ፤ አዋሸከ።

አንፏቃቂ ቅ (ስድብ) ወሬ ወዲያና ወዲህ የሚያመላልስ፤ አሳባቂ።

ፎቀፎቀ ግ የተሳከከ ወይም የተጣበቀ ነገርን ለማላቀቅ ፈገፈገ (ብዙውን ጊዜ ምጣድ ላይ የተጣበቀ እንጀራን፥ ቂጣን፡...)።

ፎቃቃ^{1} "**ፎቀቀ^{1}**" ስር ተመ.

ፎቃቃ^{2} "**ፎቀቀ^{2}**" ስር ተመ.

ፎቅ ስ ወደላይ ተደራርበው የተሰሩ ቤቶች ወይም ክፍሎች ያሉበት ህንፃ ፤ ደርብ ።

ፎተተ ግ ሸረደደ፤ አሸሟጠጠ።

ፎታች ቅ አሸሟጣጭ።

ፎቴ ስ ሶፋ።

ፎቶግራፍ (ፎቶ) ስ በካሜራ አማካኝነት በፊልም ተቀርፆ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀ ወረቀት ላይ የሚታተም የአንድ ነገር ምስል።

ፎቶግራፍ ተነሳ በካሜራ ምስሉ ተቀረፀ።

ፎቶግራፍ አነሳ በካሜራ የአንድን ነገር ምስል ቀረፀ።

ፎቶግራፍ ማንሻ ስ ካሜራ።

ፎቶግራፍ አንሺ ስ ፎቶግራፍ በማንሳት የሚተዳደር ባለሙያ።

ፎነነ ግ አፍንጫን ቆረጠ ወይም ጎመደ።

ፎናና (ፉንን) ቅ (ስድብ) አፍንጫው የተቆረጠ። 2. አፍንጫው አጭር የሆነ።

ፎከረ (ፈከረ) ግ 1.የፈፀመውን ጀብዱ በድንፋታ (ጀግንነትን ወይም ወኔን በሚቀሰቅስ ሁኔታ) ተናገረ፤ ዘራፍ አለ። 2. ዛተ፤ አስፈራራ። *ፎክሮብኛል*።

መፈክር ስ የአንድን ትግል ወይም እንቅስቃሴ የቅርብም ሆነ የሩቅ አላማና አቅጣጫ ለማመልከት በአጭር ሃረግ ወይም አረፍተ ነገር ተዘጋጅቶና በጉልህ ተፅፎ የሚታይ ወይም በቃል የሚባል መሪ ሃሳብ።

ፉከራ ስ አንድ ሰው ስለፈፀመው ጀብዱ እያነሳ በድንፋታ (ጀግንነትንና ወኔን በሚቀሰቅስ ሁኔታ) የሚለው ቃል። 2. ዛቻ።

ፉክክር ስ 1. አንዱ የሆነውን፥ ያደረገውን፡... ሌላው ለመሆን፡ ለማድረግ፡... ወይም በልጦ ለመገኘት የሚደረግ ጥረት፡ ውድድር። 2. አንተ አድርግ አንተ አድርግ መባባል።

ተፎካከረ ግ 1. አንዱ የሆነውን፥ ያደረገውን፡... ሌላው ለመሆን፡ ለማድረግ፡... ወይም በልጦ ለመገኘት ጣረ፥ ሞከረ፤ ተወዳደረ። 2. አንተ አድርግ አንተ አድርግ ተባባለ።

ተፎካካሪ ቅ 1. ተቀራራቢ፡ አቻ (በሃብት፥ በእውቀት፡...)። 2. ተወዳዳሪ።

ፎከተ ግ 1. የሰውነት ቆዳን በጣም አድርጎ አከከ። 2. (ዘይ.) በድህነት በጣም ተቸገረ። 3. ያላደገ ሳርን ከስር ፈግፍጎ አወጣ፤ ጋጠጠ።

ፎከት ስ እከክ፤ ደረመን።

ፎከታም ቅ (ስድብ) እከካም።

***ፎደፎደ**

ፎድፏዳ(ፎደፎድ) ቅ እርብትብት።

ተንፎደፎደ ግ ተንበደበደ፥ ተብረከረከ።

አንፎደፎደ ግ አንበደበደ፤ አንቀጠቀጠ።

ፎገረ^{1}(ፈገረ) ግ ከብት፤ ውሻ፥... መሬትን ፋረ፥ መነቀረ፥ ቆፈረ።

ፎገረ^{2} ግ (ያራዳ አነ.) 1. ደለለ፥ አታለለ። 2. ፎተተ፤ አሸሟጠጠ።

ፉገራ ስ 1. ማታለል፥ መደለል። 2. ፉተታ፤ ሟሸሟጠጥ።

ፎጋሪ ቅ 1. አታላይ። 2. ፎታች።

ተፎገረ ግ ተነቃበት፥ ታወቀበት።

አስፎገረ ግ አስነቃ፤ እንዲታወቅበት አደረገ።

ፎጠና ስ ወጣት፥ ሶታ፥ ኮበሌ።

ፎጣ ስ ሰውነትን፥ እጅን፥... ታጥቦ ለማድረቂያ የሚያገለግል፡ እርጥበትን መምጠጥ የሚችል ጭገር ያለው ወፍራምና ለስላሳ የሆነ ጨርቅ።

ፏ^{1} የ "ፈ" ፈደል ፍንፅቅ ዘር።

ፏ^{2}

ፏ አለ ግ 1. ድንገት በሃይል ፈሰሰ። 2. ቦግ፤ ደመቅ አለ (ብዙውን ጊዜ ለመብራት)።

ፏሸረ

አንፏሸረ ግ አዘጠዘጠ፥ አምቧተረ፡ ጉራ ነዛ።

አንፏሻሪ ቅ (ስድብ) አዘጥዛጭ፡ አምቧታሪ፡ ጉረኛ።

ፏደደ ግ እንደ ጅብ ጎንበስ ጎንበስ፡ ደፋ ቀና እያለ ገሰገሰ ፥ ሮጠ።

ፏድድ ፏድድ አለ ግ ፏደደ።

ፏገረ "**ፉገረ**"ን ተመ.

*ፏጨ

ፉጨት ስ አፍን አሞጥሙጦና ከንፈርን አጥብቦ፡ በመካከሉ ባለው ጠባብ ቀዳዳ አየር በማስወጣት የሚፈጠር ድምፅ።

አፏጨ ግ ፉጨት አሰማ።

*ፏፏ

ፏፏቴ ስ ከገደል አፋፍ ላይ በሃይልና በብዛት ተወርውሮ የሚወርድ ውሃ።

ፏፏ አለ ግ 1. በብዛት እየተንቦለቦለ ፈሰሰ። 2. ፏፏቴ የሚያሰማውን አይነት ድምፅ አሰማ።

ተንፏፏ ግ በሃይልና በብዛት ፈሰሰ፡ ወረደ፡ ተንሿሿ (ፈሳሽ)።

አንፏፏ ግ በሃይል አፈሰሰ፡ አወረደ (ፈሳሽን)።

ፐ

ፐ ከ "ፈ" ፊደል ዘር ቀጥሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል (ግእዙ ሆሄ)::

ፐርሶኔል ስ 1. የሰራተኛ ማስተዳደሪያ ክፍል::2. የሰራተኛ ማስተዳደሪያ ክፍል ሃላፊ::

ፑ የ "ፐ" ፊደል ካእብ ዘር::

ፑሽአፕ ስ በተለይ የእጅና የትከሻ አካባቢ ጡንቻዎችን ለማጠናከር ሲባል በእግር ጣቶችና በእጅ መዳፎች መሬት ላይ ተመርኩዞ ሰውነትን ቀጥ አድርጎ በመዘርጋትና የሰውነትን ክብደት ወደላይና ወደታች በማንቀሳቀስ የሚሰራ የጅምናስቲክ አይነት::

ፒ የ "ፐ" ፊደል ሳልስ ዘር::

ፒራሚድ ስ ባለሶስት ወይም ባለአራት ማእዘን መሰረት ኖሮት ጎኖቹ ወደላይ እየረዘሙ ሄደው ሾጣጣ ቅርፅ በመያዝ አንድ ቦታ ላይ እንዲጋጠሙ ተደርጎ የሚሰራ ቅርፅ (ለምሳሌ የግብፅ ፒራሚዶች)::

ፒራሚድ

ፒሳ ስ ቶርኖ ዱቄት በስሱ ተጋግሮ ይደራረብና እንደአስፈላጊነቱ የቲማቲም ስልስ ወይም ሞርታዴላ ወይም ቺዝ፥... በላዩ ላይ ተደርጎበት የሚበላ የምግብ አይነት::

ፒንሳ ስ ብረታብረቶችን ቆንጥጦ ለመያዝ፥ ለሽቦ መቁረጫ፥ ለምስማር መንቀያ፥... የሚያገለግል አነስተኛ መሳሪያ::

ፒያኖ ስ ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያ(ስእሉን የሙዚቃ መሳሪያ ስር ተመ.)::

ፒጃማ(ቢጃማ) ስ በሱሪ፥ በቀሚስ፥... መልክ የሚዘጋጅና ለመኝታ ጊዜ ብቻ የሚያገለግል ሰፋ ያለ ልብስ::

ፒፓ ስ የትንባሆ ማጨሻ::

ፓ የ "ፐ" ፊደል ራብእ ዘር::

ፓራሹት ስ ከአይሮፕላን ዘሎ አየር ላይ እየተንሳፈፉ ቀስ በቀስ ምድር ላይ ለማረፍ የሚያገለግል ጃንጥላ መሰል መሳሪያ፤ ጃንጥላ::

ፓራሹት

ፓርላማ ስ 1. የመንግስት መማክርት ጉባኤ::2. መማክርት ጉባኤ የሚያደርጉበት አዳራሽ::

ፓርቲ ስ 1. ተመሳሳይ አስተሳሰብ፥ እምነትና አላማ ባላቸው ሰዎች የሚቋቋምና የራሱ የሆነ ደንብና ፕሮግራም የሚኖረው አካል (ብዙውን ጊዜ በፖለቲካ መስመር)::2. ብዙውን ጊዜ ዳንስ የሚኖርበት ግብዣ::

ፓርክ ስ በተፈጥሮ የሚገኝ፥ ልዩልዩ አውሬዎችና አእዋፍ የሚኖሩበት፤በመንግስት ተከልሎ ሰዎች እንዲጎበኙት የሚደረግ ቦታ::

ፓስቲ ስ የቶርኖ ዱቄት ሊጥ በስሱ ከተዳመጠ በሂላ በዘይት የሚጠበስ የምግብ አይነት::

ፓስቲኒ ስ የማካሮኒ አይነት::

ፓስታ ስ በተወሰነ ቁመትና ውፍረት ተሽምልሎ ከተቆራረጠ የስንዴ ዱቄት ሊጥ ተዘጋጅቶ ከደረቀ በሂላ ተቀቅሎ የሚበላ የምግብ አይነት::

ፓስታል ፉርኖ ስ እንደ ዳቦ ሆኖ ከፓስታ የሚሰራ ምግብ::

ፓስፖርት ስ ስለአንድ ሰው ማንነት ተፈላጊውን መግለጫ የያዘና ግለሰቡ ከአገር ውጭ እንዲዘዋወር የሚያስችለው በመንግስት የሚሰጥ ሰነድ ወይም መታወቂያ::

ፓትርያርክ ስ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ከፍተኛው ማእረግና ስልጣን ያለው መንፈሳዊ መሪ ወይም መንፈሳዊ አባት::

ፓኬት ስ መጠኑ አነስተኛ የሆነ እቃ የያዘ ጥቅል፤ እሽግ::

ፓኮ ስ ዝ.ከ.

ፓይለት ስ አይሮፕላን አብራሪ::

ፓፓያ (ፓፓዬ) ስ ለስላሳና ጣፋጭ የሆነ፤ ባብዛኛው ሞላላ ቅርፅ ያለውና ከቦቁር አዝሙድ ከፍ የሚሉ ጥቋቁር ዘሮች ያሉት የሚበላ የፍራፍሬ አይነት፤ ፍሬውን የሚያፈራው ተክልም ፓፓያ ይባላል::

ፔ የ "ፐ" ፊደል ሃምስ ዘር::

ፔሬድ ስ ክፍለ ጊዜ::

ፔርሙዝ ስ የተፈላ ፈሳሽ (ሻይ፣ ቡና፣...) ሳይቀዘቅዝ ለረዥም ጊዜ ወይም ለተወሰነ ሰአት በውስጡ እንዲቆይ የሚያደርግ እቃ::

ፔቲካሽ ስ ጥቃቅን እቃዎችን ለመግዛት ወጪ የሚሆን ገንዘብ (በመስሪያ ቤት አካባቢ)::

ፔኒሲሊን ስ ጀርሞች እንዳያድጉ ወይም

እንዳያራቡ የሚከላከል ፀረ ባክቴሪያ የሆነ መድሃኒት።

ፔዳል ስ ብስክሌት በሚነዳበት ጊዜ የእግር ጫማ የሚያርፍበትና ካቴናውን ለማሽከርከር የሚረዳ መርገጫ።

ፔዳጎጂ ስ የማስተማር ሙያ ሳይንስ።

ፕሉቶ ስ ከፀሃይ ጀምሮ ሲቆጠር በርቀት ዘጠነኛ ሆኖ የሚገኝና በፀሃይ ዙሪያ ከሚሽከረከሩት ፕላኔቶች አንዱ (በተጨማሪ ፕላኔትን ተመ.)።

ፕላስተር ስ በአንድ በኩል ሙጫነት ያለው ሆኖ ከጨርቅ ወይም ከፕላስቲክ የሚሰራ ማጣበቂያ።

ፕላስቲክ ስ በቀላሉ ሊተጣጠፍና ልዩ ልዩ ቅርፅ ሊይዝ የሚችል፣ ውሃ የማያሳልፍ፣ እሳት በቀላሉ የማያቀልጠውና እንደ ዝናብ ልብስ፣ ባልዲ፣ ጀሪካን፣... ያሉ ነገሮች የሚሰሩበት በተፈጥሮ ወይም በሰው ሰራሽነት የሚገኝ ቁስ።

ፕላቲነም ስ ግራጫ መልክ ያለውና ከብረት ክፍል የሆነ ንጥረ ነገር።

ፕላኔት ስ. እንደ መሬት ያለ፣ በፀሃይ ዙሪያ የሚዞርና በህዋ ውስጥ የሚገኝ አካል (ሜርኩሪ፣ ቬኑስ፣...)።



ፕላኔት

ፕላን ስ 1. እቅድ 2. ንድፍ።

ፕላን አወጣ ፕላን (እቅድ) ነደፈ፣ አዘጋጀ።

ፕላዝማ ስ በሰውነት ውስጥ የደም ሴሎችን የሚሸከም ቢጫ መሰል ፈሳሽ።

ፕሬስ ስ 1. ጋዜጦች፣ መፅሄቶች፣ የሬዲዮና የቴሌቪዥን ዘገባዎች።2. በጋዜጠኝነት ሙያ የተሰማሩ ሰራተኞች ስራቸውን የሚያካሂዱበት መስሪያቤት ወይም ድርጅት።

የፕሬስ መግለጫ በመንግስት አካል፣ በፖለቲካ ፓርቲ፣... የሚሰጥና በመገናኛ ብዙሃን የሚገለፅ ኦፊሲላዊ መግለጫ።

የፕሬስ ነፃነት ህዝብ ሊያውቃቸው የሚገቡ ዜናዎችንና ሚዛናዊ አስተያየቶችን ያለምንም ተፅእኖና ፍራቻ በነፃ የመግለፅ መብት።

ፕሬስ ኮንፈረንስ ስለአንድ አቢይ ጉዳይ በሚመለከተው አካል በኩል በመገናኛ ብዙሃን ለህዝብ ይፋ ለማድረግ የሚካሄድ ቃለ ምልልስ፣ ጋዜጣዊ መግለጫም ይባላል።

ፕሬዚዲየም ስ በዋናዋና የመንግስትና የፓርቲ ስብሰባዎች ወይም ጉባኤዎች ላይ ስብሰባዎችን ወይም ጉባኤዎችን የሚመራና አመራር የሚሰጥ የሰዎች ስብስብ ወይም የበላይ አካል።

ፕሬዚዳንት ስ የአንድ አገር ወይም ድርጅት፣... የበላይ መሪ፣ ሹም።

ፕሮቲን ስ እንደስጋና እንቁላል ባሉ የምግብ አይነቶች ውስጥ የሚገኝና ለሰውነት ግንባታና ለጤንነት በጣም አስፈላጊ የሆነ አልሚ ምግብ።

ፕሮቴስታንት ስ 1. በዘመነ ተሃድሶ (ሪፎርሜሽን) ከሮማ ቤተክርስቲያን ተገንጥሎ የወጣ የክርስትና ሃይማኖት ቅርንጫፍ። 2. ከላይ የተጠቀሰው ሃይማኖት ተከታይ።

ፕሮቶኮል ስ በመንግስት አመራር አባላትና አካላት አካባቢ ልዩ ልዩ ክንዋኔዎችንና ስነስርአቶችን የሚመለከት የማእረግ ደረጃ ቅደም ተከተል።

የፕሮቶኮል ስምምነት ስ በሃገሮች መካከል የሚደረግ የትምህርት፣ የባህል፣ የኢኮኖሚ፣... ስምምነት፣ ውለታ (ውል)።

የፕሮቶኮል ሹም ስ የመንግስትን የፕሮቶኮል ስነስርአት የሚያስከብር ሃላፊ።

ፕሮጀክተር ስ ተንቀሳቃሽ ወይም የማይንቀሳቀሱ የፊልም ስእሎችን በነጭ ሰሌዳ ላይ ለማሳየት የሚያገለግል መሳሪያ።

ፕሮጀክት ስ ከለት ተእለት መደበኛ ስራ በተለየ ሁኔታ አንድን ስራ ለማከናወን የተዘረጋ እቅድ።

ፕሮግራም(መርሃ ግብር) ስ 1. አንድ ተግባር የሚከናወንበት የተወሰነ የጊዜ ክልል። *የቴሌቪዥን ፕሮግራም ስንት ሰአት ላይ ይጀምራል?* 2. እቅድ። *ኑሮውን በፕሮግራም የሚመራ ሰው ነው።* 3. የተወሰነ የጊዜ ርዝመት የተመደበላቸው ድርጊቶች ዝርዝር። *የስብሰባው ፕሮግራም ደርሶሃል?*

ፕሮግራም አወጣ እቅድ ነደፈ፣ የተለያዩ ስራዎች በቅደም ተከተል የሚሰሩበትን ጊዜ መደበ።

ፕሮፌሰር ስ በዩኒቨርስቲ፣ በኮሌጅ፣ በሙያ ጥናት ተቋም ውስጥ በሚያደርገው ምሁራዊ ስራ (በጥናትና ምርምር፣ በማስተማር፣...) ከፍተኛ አስተዋፅኦ ላደረገ ሊቅ ወይም ምሁር የሚሰጥ ማእረግ።

ፕሮፌሽናል ቅ በአንድ የሙያ ዘርፍ ስልጥና በቂ እውቀት ያለውና በዚያው ሙያ የሚተዳደር፤ ባለሙያ።

ፕሮፌሽን ስ በስልጠና የሚገኝ ሙያ።

ፕሮፓጋንዳ ስ አንድን የተወሰነ ሃሳብ ወይም እምነት በተለያየ ስልትና የስርጭት ዘዴ በማስተላለፍ የህዝብን አስተያየት ለመሳብ፣ ድጋፍ ለማግኘትና አመለካከትን ለመቀየር የሚደረግ ጥረት።

ፖ የ "ፐ" ፊደል ሳብእ ዘር።

ፖለቲካ ስ ከስልጣንና አገር ከማስተዳደር አኳያ አንድ መንግስት ከሚያስተዳድረው ህዝብና ከሌሎች መንግስታት ጋር ያለው ግንኙነት ሁኔታ፥ አመለካከት፥ እንቅስቃሴ፤ ስነመስተዳድር ወይም የመስተዳድር ሳይንስ።

ፖለቲካ ተናጋሪ በስልጣን ላይ ያለውን መንግስት የሚነቅፍና አመፅ ሊያስነሳ የሚችል ነገር ተናጋሪ።

የፖለቲካ ጥገኛ ስ በፖለቲካ ምክንያት ከአገሩ ተሰዶ በባእድ አገር የሚኖር ሰው።

የፖለቲካ ጥገኝነት በፖለቲካ ምክንያት ከራስ አገር በመሰደድ በባእድ አገር መኖር።

ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ስ በምርት ሂደት ውስጥ በሰዎች መካከል የሚፈጠረውን የኢኮኖሚ ግንኙነት (ምርትን፥ ክፍፍልን፥ ልውውጥንና ፍጆታን) የሚገዙ ማህበራዊ ህጎችን የሚያጠና ሳይንስ።

ፖለቲከኛ ስ የፖለቲካ ስራ የሚሰራ የፖለቲካ ሰው።

ፖሊሲ ስ በመንግስት፣ በፖለቲካ ፓርቲ ወይም በኩባንያ የሚዘጋጅ የተግባር መመሪያ።

ፖሊስ ስ ሰላምና ፀጥታን እንዲሁም ህግን የሚያስከብር፣ ወንጀልን የሚከላከል፣ በመንግስት የተቀጠረ መለዮ ለባሽ።

ፖሊስ ጣቢያ ስ ፖሊስ ተግባሩን የሚያከናውንበት ፅህፈት ቤት።

ፖሊዮ ስ ልምሻ።

ፖምፕ ስ የመኪና፥ የብስክሌት ጎማን፥...አየር ለመሙላት የሚያገለግል መሳሪያ።

ፖርቶመጋሊያ ስ እንደ ታክሲ፥ አውቶቡስ፥... ባሉ መኪናዎች አናት ላይ የሚገጠምና ለእቃ መጫኛ ወይም ማስቀመጫ የሚያገለግል የመኪና እቃ።

ፖስተር ስ አንድን ነገር ለማስተዋወቅ ወይም ለማስተማር ሲባል ብዙ ህዝብ ሊያየው በሚችልበት ቦታ በትልልቅ ወረቀት የሚለጠፍ የማስተማሪያ ወይም የማስተዋወቂያ ስእልና ፅሁፍ።

ፖስታ ስ ብዙውን ጊዜ በፖስታ ቤት በኩል ከአንድ ቦታ ወደሌላ ቦታ የሚላክ ፅሁፍ ወይም መጠኑ አነስተኛ የሆነ ሌላ እቃ የሚከተትበት የተለያየ መጠን ያለውና ሊታሸግ የሚችል የወረቀት ከረጢት።

ፖስተኛ ስ ፖስታ የሚያመላልስ ሰራተኛ።

[የ] ፖስታ ሳጥን ስ 1. በፖስታ ቤት በኩል የሚላኩ ደብዳቤዎች፥ መፅሄቶች፥... የሚከተቱበት ወይም የሚጠራቀሙበት ሳጥን። 2. የሚላኩላቸው ደብዳቤዎች፥ መፅቶች፥... ይጠራቀሙበት ዘንድ ተገልጋዮች ከፖስታ ቤት የሚከራዩትና መለያ ቁጥር ያለው ሳጥን።

ፖስታ ሳጥን ቁጥር ስ ለፖስታ ሳጥን የሚሰጥ መለያ ቁጥር።

ፖስታ ቤት ስ የአገልግሎት ዋጋ በማስከፈል ፖስታዎችን እየተቀበለ በአድራሻቸው የሚልክ፥ የሚያስተላልፍ፥ የሚያድል መንግስታዊ መስሪያ ቤት።

ፖታሽ ስ ሳሙና፥ ማዳበሪያ፥... ለመስራት የሚያገለግል ኬሚካል።

ፖፖ ስ የሽንት እቃ፤ መክፈያ።

አባሪ

የአእማድ ግሶች ከነቅዕልና ስሞቻቸዉ ጋር። (የቃሉን ፍቺ በአንፃሩ ከሚገኘውና በትእምርተ ጥቅስ ውስጥ ከሰፈረው መነሻ ቃል ስር ተመልከት።)

ተለ

ተለመሰሰ	-"ለመሰሰ"
ተለመነ	-"ለመነ"
ተለመደ	"ለመደ"
ተለመጠ	"ለመጠ"^{1}
ተለመጠጠ	-"ለመጠጠ"^{2}
ተለማመነ	"ለመነ"
ተለማመደ	-"ለመደ"
ተለማመጠ	-"ለመጠ"
ተለማማጅ	-"ለመደ"
ተለማማጭ	-"ለመጠ"
ተለማኝ	-"ለመነ"
ተለሳለሰ	-"ለሰለሰ"
ተለሸለሸ	-"ለሸለሸ"
ተለቀሰ	"*ለቀሰ"
ተለቀቀ	-"ለቀቀ"
ተለቀተ	-"ለቀተ"
ተሊቃ	-"*ሊቃ"
ተሊቃለቀ	-"ለቃለቀ"
ተሊቃሽ	-"*ለቀሰ"
ተለባለበ	-"ለበለበ"
ተለባበሰ	-"ለበሰ"
ተለከፈ^1	-"ለከፈ"
ተለከፈ^2	-"*ለከፈ"
ተለካ	-"ለካ"
ተለካከፈ	-"ለከፈ"
ተለካካ	-"ለካ"
ተለኮሰ	-"*ለኮሰ"
ተለወጠ	-"ለወጠ"
ተለዋወሰ	-"ለወሰ
ተለዋወጠ	-"ለወጠ"
ተለዋዋጭ	-"ለወጠ"
ተለዋጭ	-"ለወጠ"
ተለዘበ	-"ለዘበ"
ተለየ	-"ለየ"
ተለያየ	-"ለየ"
ተለደፈ	-"ለደፈ"

ተሰገሰ	-"ሰገሰ"
ተሰጎመ	-"ሰጎመ"
ተሰጠሰጠ	-"ሰጠሰ"
ተሰጠበ	-"ሰጠበ"
ተሰጠቀ	-"ሰጠቀ"
ተሰጠጠ	-"ሰጠጠ^1"
ተሰጠፈ	-"ሰጠፈ"
ተሰጣጠቀ	-"ሰጠቀ"
ተሰጣፈ	-"ሰጠፈ"
ተሰፈፈ	-"ሰፈፈ"
ተሰፋ	-"ሰፋ"
ተሰፋሰፈ	-"ሰፈሰፈ"
ተሰፋደደ	-"ሰፈደደ"
ተሰፋጨቀ	-"ሰፈጨቀ"
ተሳለቀ	-"አለቀ"
ተሳለፈ	-"አለፈ"
ተሳሳሰ	-"ሳሰ"
ተሳሳከ	-"ሳከ"
ተሳሳኪ	-"ሳከ"
ተሳሳጠ	-"ሳጠ^1"
ተሳሳፈ	-"አሳፈ"
ተሳመደ	-"ሰመደ"
ተሳቀሰ	-"*ሰቀሰ"
ተሳቀቀ	-"ሰቀቀ"
ተሳበሰ	-"ሰበሰ"
ተሳተመ	-"ሰተመ"
ተሳከ	-"ሳከ"
ተሳከከ	-"ሳከከ"
ተሳከፈ	-"ሰከፈ"
ተሳካፈ	-"ሰከፈ"
ተሳወሰ	-"*ሰወሰ"
ተሳዘዘ	-"ሰዘዘ"
ተሳገደ	-"*ሰገደ"
ተሳገገ	-"ሰገገ"
ተሳገጠ	-"*ሰገጠ"
ተሳጋ	-"ሰጋ^1"
ተሳጠ^1	-"ሳጠ^1"
ተሳጠ^2	-"ሳጠ^2"
ተሳጠ^3	-"ሳጠ^3"
ተሳጠቀ	-"ሰጠቀ"
ተሳጨ	-"ሳጨ"
ተሳፈ	-"ሳፈ"
ተሳፋ	-"ሰፋ"
ተሏመጠመጠ	-"ለመጠ^1"

ተልክሰከሰ	-"*ለከሰከሰ"
ተልክፈከፈ	-"ለከፈ"
ተልኮሰኮሰ	-"*ለኮሰ"
ተልኮፈኮፈ	-"ለኮፈ"
ተልገዘገዘ	-" *ለገዘገዘ"
ተልጎመጎመ	-"ለጎመ"
ተልፈሰፈሰ	-"*ለፈሰፈሰ"

ተመ

ተመለሰ	-"መለሰ"
ተመለከ	-"*መለከ"
ተመለከተ	-"*መለከተ"
ተመለካከተ	-"*መለከተ"
ተመለጠ	-"መለጠ"
ተመላለሰ	-"መለሰ"
ተመላለጠ	-"መለጠ"
ተመላላሸ	-"መለሰ"
ተመላሸ	-"መለሰ"
ተመላከተ	-"*መለከተ"
ተመልካች	-"*መለከተ"
ተመረረ	-"መረረ"
ተመረቀ	-"መረቀ"
ተመረተ	-"መረተ"
ተመረከዘ	-"*መረከዘ"
ተመረዘ	-"መረዘ"
ተመሪ	-"መራ"
ተመራ	-"መራ"
ተመራመረ	-"መረመረ"
ተመራማሪ	-"መረመረ"
ተመራቂ	-"መረቀ"
ተመራጭ	-"መረጠ"
ተመሰለ	-"መሰለ"
ተመሰቃ	-"*መሰቃ"
ተመሳቀለ	-"*መሰቀለ"
ተመሳገነ	-"* መሰገነ"
ተመሰጠ	-"መሰጠ"
ተመሳሰለ	-"መሰለ"
ተመሳሳይ	-"መሰለ"
ተመሳከረ	-"መሰከረ"
ተመሳጠረ	-" *መሰጠረ"
ተመሰገነ	-" *መሰገነ
ተመቀኘ	-" *መቀኘ"
ተመቻ	-"መቻ"
ተመቸ	-" *መቸ"
ተመቻቸ	-" *መቸ"
ተመነሸ	-"መነሸ"
ተመንደገ	-"መንደገ"
ተመንጠቀ	-"መንጠቀ"
ተመናመነ	-"መነመነ"
ተመናቀረ	-"መነቀረ"
ተመናቸከ	-"መነቸከ"
ተመናጨቀ	-"*መነጨቀ"
ተመኘ	-"*መኘ"
ተመከረ	-"መከረ"
ተመካ	-"*መካ"
ተመካኘ	-"*መከኘ"
ተመካከረ	-"መከረ"
ተመዘበረ	-"መዘበረ
ተመዘነ	-"መዘነ"
ተመዘዘ	-"መዘዘ"
ተመዘገበ	-"መዘገበ"
ተመደበ	-"መደበ"
ተመገበ	-"መገበ"
ተመጠነ	-"መጠነ"
ተመጠጠ	-"መጠጠ"
ተመጣጠነ	-"መጠነ"
ተመጣጣኝ	-"መጠነ"
ተመጨለሰ	-"መጨለሰ"
ተመፀወተ	-"መፀወተ"
ተመፃደቀ	"*መፀደቀ"
ተመፃዳቂ	-"*መፀደቀ"
ተመፅዋች	-"መፀወተ"
ተሙለጨለጨ	"ሟለጨ"
ተማለደ	"ማለደ"
ተማመነ	-"አመነ"
ተማማረ	"*መሃረ"
ተማረረ	-"መረረ"
ተማሰለ	-"መሰለ"
ተማታ	"መታ"
ተማከረ	-"መከረ"
ተማዘዘ	-"መዘዘ"
ተማገረ	-"ማገረ"
ተማፀነ	-"*ማፀነ"
ተምቧቧ	-"*ቧቧ"
ተምታታ	-"መታ"
ተምነሸነሸ	-"መነሸነሸ"
ተምዘገዘገ	-"*መዘገዘገ"
ተምዘገዘጊ	"*መዘገዘገ"
ተሞላ	-"ሞላ"
ተሞላቀቀ	-"*ሞለቀቀ"
ተሞላፈጠ	-"*ሞለፈጠ"
ተሞሸለቀ	-"ሞሸለቀ"
ተሞሸረ	-"ሞሸረ"
ተሞሸለቀ	-"ሞሸለቀ"
ተሞናሞነ	-"*ሞነሞነ"
ተሞናደለ	"*ሞነደለ"
ተሞኘ	"*ሞኘ"

ተሞከሸ	-"*ሞከሸ"
ተሞጸሞጸ	-"*ሞደሞደ"
ተሞገሰ	"*ሞገሰ"
ተሞጣሞጠ	-"ሞጣሞጠ"
ተሟላ	-"ሞላ"
ተሟሟቀ	"ሞቀ"
ተሟሟተ	"ሞተ"
ተሟገተ	-"ሞገተ"
ተሟጠጠ	-"ሟጠጠ"

ተረ

ተረመረመ	-"ረመረመ"
ተረማመደ	-"*ረመደ"
ተረሳ	"ረሳ"
ተረሳሳ	-"ረሳ"
ተረሸነ	-"ረሸነ"
ተረቀቀ	-"ረቀቀ"
ተረበሸ	-"ረበሸ"
ተረበረበ	"ረበረበ"
ተረባረበ	-"ረበረበ"
ተረባበሸ	-"ረበሸ"
ተረታ	-"ረታ"
ተረታታ	-"ረታ"
ተረከበ	-"*ረከበ^{2}"
ተረካቢ	-"*ረከበ^{2}"
ተረካከበ	-"*ረከበ^{2}"
ተረጸ	-"*ረጸ"
ተረጆ	-"ረጸ"
ተረገዘ	-"*ረገዘ"
ተረጋገጠ^{1}	"ረገጠ"
ተረጋገጠ^{2}	-"*ረገጠ"
ተረጋጋ	"ረጋ"
ተረጠበ	-"ረጠበ^{2}"
ተረጠጠ	"ረጠጠ"
ተረጣቢ	-"ረጠበ^{2}"
ተረጨ	-"ረጨ"
ተረፈረፈ	-"ረፈረፈ"
ተራመደ	-"*ረመደ"
ተራማጅ	-"*ረመደ"
ተራረደ	-"አረደ"
ተራራቀ	-"ራቀ"
ተራቀቀ	-"ረቀቀ"
ተራቆተ	-"*ራቆተ"
ተራበ	-"ራበ"
ተራበሸ	-"ረበሸ"
ተራባ	"ረባ"
ተራኮተ	-"*ረኮተ"
ተራወጠ	-"*ረወጠ"
ተራዘመ	-"ረዘመ"
ተራገመ	-"ረገመ"
ተራገበ	-"*ረገበ"
ተራገጠ	"ረገጠ"
ተራገፈ	-"ረገፈ"
ተራጋጭ	-"ረገጠ"
ተራጨ	"ረጨ"
ተርመሰመሰ	-"*ረመሰመሰ"
ተርመጠመጠ	-"ረመጠ"
ተርሞጠሞጠ	-"ረመጠ"
ተርበተበተ	"*ረበተበተ"
ተርበደበደ	-"*ረበደበደ"
ተርከፈከፈ	-"*ረከፈከፈ"
ተርገበገበ	-"*ረገበ"
ተርገደገደ	-"*ረገደ"
ተርገፈገፈ	-"*ረገፈገፈ"
ተሯሯጠ	-"ሮጠ"

ተሰ

ተሰለሰ	-"ሰለሰ"
ተሰለሰለ	"ሰለሰ"
ተሰለቀ	-"*ሰለቀ"
ተሰለበ	-"ሰለበ"
ተሰለቸ	-"ሰለቸ"
ተሰለፈ	"ሰለፈ"
ተሰላቸ	-"ሰለቸ"
ተሰላፊ	-"ሰለፈ"
ተሰመረ	"*ሰመረ"
ተሰሚ	-"ሰማ^{1}"
ተሰማ	-"ሰማ^{1}"
ተሰማራ	-"*ሰማራ"
ተሰረረች	-"ሰረረ"
ተሰረሰረ	-"ሰረሰረ"
ተሰረቀ	-"ሰረቀ^{1}"
ተሰረዘ	-"ሰረዘ"
ተሰረየ	-"*ሰረየ"
ተሰረገ	-"ሰረገ^{1}"
ተሰረጎደ	-"ሰረጎደ"
ተሰሬ	-"ሰራ^{2}"
ተሰራ^{1}	-"ሰራ^{1}"
ተሰራ^{2}	-"ሰራ^{2}"
ተሰራጨ	-"*ሰራጨ"
ተሰቀለ	"ሰቀለ"
ተሰቀቀ	-"ሰቀቀ^{1}"
ተሰቃየ	-"*ሰቀየ"
ተሰበረ	"ሰበረ"
ተሰበሰበ	-"ሰበሰበ"
ተሰበከ	-"ሰበከ"
ተሰባሪ	-"ሰበረ"

ተሰባሰበ	-"ሰበሰበ"
ተሰባቀለ	"*ሰበቀለ"
ተሰባበረ	"ሰበረ"
ተሰባጠረ	-"ሰበጠረ"
ተሰነቀ	"ሰነቀ"
ተሰነቀረ	"ሰነቀረ"
ተሰነበጠ	-"ሰነበጠ"
ተሰነባበተ	-"ሰነበተ"
ተሰነዘረ	-"ሰነዘረ^{1}"
ተሰነገ^{1}	"ሰነገ^{1}"
ተሰነገ^{2}	-"ሰነገ^{2}"
ተሰነጠቀ	"ሰነጠቀ"
ተሰነጣጠቀ	-"ሰነጠቀ"
ተሰናሰለ	-"*ሰነሰለ"
ተሰናበተ	-"ሰነበተ"
ተሰናኘ	-"*ሰነኘ"
ተሰናከለ	-"ሰነከለ"
ተሰነዘረ	"ሰነዘረ^{1}"
ተሰናዳ	-"*ሰነዳ"
ተሰኘ	-"*ሰኘ"
ተሰካ	-"ሰካ"
ተሰካካ	-"ሰካ"
ተሰወረ	-"ሰወረ"
ተሰዋ	-"ሰዋ"
ተሰየመ	-"ሰየመ"
ተሰየፈ	"ሰየፈ"
ተሰደረ	-"ሰደረ"
ተሰደበ	-"ሰደበ"
ተሰደደ	-"ሰደደ"
ተሰገሰገ	"ሰገሰገ"
ተሰገጠ	-"ሰገጠ"
ተሰጠ	"ሰጠ"
ተሰፈረ	"ሰፈረ^{1}"
ተሳለ	-"*ሳለ"
ተሳለመ	-"*ሰለመ"
ተሳለቀ	-"*ሰለቀ"
ተሳለ	"ሰላ^{2}"
ተሳሳ	"*ሳሳ"
ተሳሳሚ	"*ሰላመ"
ተሳማ	-"ሰማ^{1}"
ተሳሰረ	"አሰረ"
ተሳሰበ	-"አሰበ"
ተሳቀቀ	-"ሰቀቀ"
ተሳሳበ	-"ተሳበ"
ተሳሳተ	-"ሳተ"
ተሳበ	-"ሳበ"
ተሳበበ	-"*ሰበበ"
ተሳቢ	"ሳበ"
ተሳተ	-"ሳተ"
ተሳተፈ	-"*ሰተፈ"
ተሳታፊ	-"*ሰተፈ"

ተሳነፈ	"ሰነፈ"
ተሳከረ	-"ሰከረ"
ተሳካ	"ሰካ"
ተሳደበ	-"ሰደበ"
ተሳደደ	"ሰደደ"
ተሳዳቢ	-"ሰደበ"
ተሳገ	"ሳገ"
ተሳፈረ	"ሰፈረ^{2}"
ተሰለመለመ	-"ሰለመ^{2}"
ተሰለከለከ	"*ሰለከለከ"
ተሰመነመነ	"*ሰመነመነ"
ተሰማሚ	"ሰማ^{1}"
ተሰማማ	-"ሰማ^{1}"
ተሰረቀረቀ	-"*ረቀረቀ"
ተሰረገረገ	-"ሰረገ^{2}"
ተሰበደበደ	-"*ሰበደበደ"
ተስተናገደ	-"*ነገደ"
ተሰገመገመ	-"*ገመገመ"
ተሰገበገበ	"*ሰገበገበ"
ተሰፈነጠረ	-"ፈነጠረ"
ተሰፈንጣሪ	"ፈንጣረ"
ተሰፋፈ	"ሰፋ^{2}"
ተሰፋፋ	-"ሰፋ^{2}"

ተሸ

ተሸለመ	-"ሸለመ"
ተሸለሸለ	"ሸለሸለ"
ተሸለቀቀ	-"ሸለቀቀ"
ተሸለተ	-"ሸለተ"
ተሸለፈፈ	"ሸለፈፈ"
ተሸላለመ	-"ሸለመ"
ተሸላሚ	-"ሸለመ"
ተሸመቀቀ	-"ሸመቀቀ"
ተሸማቀቀ	-"ሸመቀቀ"
ተሸረሸረ	-"ሸረሸረ"
ተሸረከተ	-"ሸረከተ"
ተሸረጠ	"*ሸረጠ"
ተሸረፈ	"ሸረፈ"
ተሸራሞጠ	-"ሸረሞጠ"
ተሸራረፈ	-"ሸረፈ"
ተሸራሸ	"*ሸረሸ"
ተሸራሸረ	"ሸረሸረ"
ተሸሸገ	-"ሸሸገ"
ተሸበለለ	-"ሸበለለ"
ተሸበረ	"*ሸበረ"
ተሸበሸበ	-"ሸበሸበ"
ተሸበበ	-"ሸበበ"
ተሸባሪ	"*ሸበረ"
ተሸነሸነ	-"ሸነሸነ"

ተሸነቀረ	"ሸነቀረ"
ተሸነቆረ	-"ሸነቀረ"
ተሸነተረ	"ሸነተረ"
ተሸነገለ	"ሸነገለ"
ተሸነፈ	-"*ሸነፈ"
ተሸናገረ	-"*ሸነገረ"
ተሸናፈ	-"*ሸነፈ"
ተሸና	-"ሸና"
ተሸከመ	"*ሸከመ"
ተሸከሸከ	"ሸከሸከ"
ተሸካሚ	-"*ሸከመ"
ተሸወደ	-"ሸወደ"
ተሸደሸደ	"ሸደሸደ"
ተሸጋሸገ	-"*ሸገሸገ"
ተሸጋገረ	-"*ሻገረ"
ተሸጋጋሪ	-"*ሻገረ"
ተሸጎረ	-"ሸጎረ"
ተሸጎጠ	-"ሸጎጠ"
ተሸጠ	"ሸጠ"
ተሸፈነ	-"ሸፈነ"
ተሸፋፈነ	-"ሸፈነ"
ተሹሉክሉክ	-"ሾለከ"
ተሻለ	"*ሻለ"
ተሻማ	"*ሻማ"
ተሻረ^1	-"ሻረ^1"
ተሻረ^2	-"ሻረ^2"
ተሻረከ	"*ሻረከ"
ተሻሸ	-"አሸ"
ተሻሻለ	-"*ሻለ"
ተሸተተ	-"ሸተተ"
ተሻኮተ	"*ሻኮተ"
ተሻገረ	"*ሻገረ"
ተሻጋሪ	"*ሻገረ"
ተሻጠ	" ሻጠ"
ተሽመደመደ	-"*ሽመደመደ"
ተሽሞነሞነ	-"*ሽሞነሞነ"
ተሽረከረከ	-"*ሽረከረከ"
ተሽቀነደረ	-"*ቀነደረ"
ተሽቀነጠረ	-"*ቀነጠረ"
ተሽቀዳደመ	"ቀደመ"
ተሽቆለቆለ	-" ቆለቆለ"
ተሽቆጠቆጠ^1	-"*ሽቆጠቆጠ^1"
ተሽቆጠቆጠ^2	-"*ሽቆጠቆጠ^2"
ተሽበለበለ	-"*ሽበለበለ"
ተሽከረከረ	-"*ሽከረከረ"
ተሽከርካሪ	-"*ሽከረከረ"
ተሽኮመኮመ	-"*ሽኮመኮመ"
ተሽኮረመመ	-"*ሽኮረመመ"
ተሽኮነተረ	-"*ኮነተረ"
ተሽኮንታሪ	-"*ኮነተረ"

ተሾለከ	-"ሾለከ"
ተሾመ^1	"ሾመ^1"
ተሾመ^2	-"ሾመ^2"
ተሾቀ	-"ሾቀ"
ተሾፈ	"*ሾፈ"
ተሿሚ	-"ሾመ^1"

ተቀ

ተቀለመ	"*ቀለመ"
ተቀለበ	"ቀለበ^1"
ተቀለበሰ	"ቀለበሰ"
ተቀለደ	-"ቀለደ"
ተቀለጠመ	"ቀለጠመ"
ተቀለጣጠመ	-"ቀለጠመ"
ተቀለጣጠፈ	-"ቀለጠፈ"
ተቀላለደ	-"ቀለደ"
ተቀላቀለ	"ቀላቀለ"
ተቀላቢ	-"ቀለበ^1"
ተቀላጠፈ	-"ቀለጠፈ"
ተቀመጠ	-"*ቀመጠ"
ተቀመጠለ	-"ቀመጠለ"
ተቀመጣጠለ	-"ቀመጠለ"
ተቀማመሰ	-"ቀመሰ"
ተቀማቀመ	-"*ቀመቀመ"
ተቀማጠለ	-"*ቀማጠለ"
ተቀማጭ	-"*ቀመጠ"
ተቀረማመተ	-"*ቀረመተ"
ተቀረቀረ	"ቀረቀረ"
ተቀረደደ	-"ቀረደደ"
ተቀረፈ	-"ቀረፈ"
ተቀረፈተ	"ቀረፈተ"
ተቀራመተ	-"*ቀራመተ"
ተቀራረበ	-"ቀረበ"
ተቀራራቢ	-"ቀረበ"
ተቀራደደ	"ቀረደደ"
ተቀሰረ	-"ቀሰረ"
ተቀሰቀሰ	-"ቀሰቀሰ"
ተቀሰፈ	"ቀሰፈ"
ተቀሸረ	-"ቀሸረ"
ተቀቀለ	-"ቀቀለ"
ተቀበለ	"*ቀበለ"
ተቀበረ	-"ቀበረ"
ተቀበተተ	-"ቀበተተ"
ተቀባ	-"ቀባ"
ተቀባበለ	-"*ቀበለ"
ተቀባባ	"ቀባ"
ተቀተረ^1	-"ቀተረ^1"
ተቀተረ^2	"ቀተረ^2"
ተቀተረ^3	"ቀተረ^3"

ተቀታተረ	-"*ቀተረ"
ተቀነሰ	-"ቀነሰ"
ተቀነባበረ	-"*ቀነበረ"
ተቀነዘፈ	-"ቀነዘፈ"
ተቀነደለ	-"ቀነደለ"
ተቀነጠሰ	-"ቀነጠሰ"
ተቀነጠበ	-"ቀነጠበ"
ተቀነጣጠበ	-"ቀነጠበ"
ተቀናሸ	-"ቀነሰ"
ተቀናነሰ	-"ቀነሰ"
ተቀናበረ	-"*ቀነበረ"
ተቀናጀ	-"*ቀነጀ"
ተቀናጣ	"ቀነጣ"
ተቀኘ	-"*ቀኘ"
ተቀዛቀዘ	-"ቀዘቀዘ"
ተቀየመ	"*ቀየመ"
ተቀየረ	-"ቀየረ"
ተቀየጠ	-"ቀየጠ"
ተቀያረ	-"ቀየረ"
ተቀያየመ	-"*ቀየመ"
ተቀያየረ	-"ቀየረ"
ተቀያያረ	-"ቀየረ"
ተቀያየጠ	-"ቀየጠ"
ተቀደመ	-"ቀደመ"
ተቀዳሚ	-"ቀደመ"
ተቀዳጪ	-"ቀዳ"
ተቀዳደመ	-"ቀደመ"
ተቀዳደደ	-"ቀደደ"
ተቀዳጀ	-"*ቀደጀ"
ተቀዳጅ	-"ቀደደ"
ተቀጠጠ	-"ቀጠጠ^{2}"
ተቀጠፈ	-"ቀጠፈ"
ተቀጣ	"ቀጣ"
ተቀጣይ	-"ቀጠለ"
ተቀጣጠለ^{1}	-"ቀጠለ"
ተቀጣጠለ^{2}	"*ቃጠለ"
ተቀጣጠረ	-"ቀጠረ^{4}"
ተቀጣጠበ	-"ቀጠበ"
ተቀጥላ	-"ቀጠለ"
ተቀጨ	-"ቀጨ^{1}"
ተቀፅላ	-"ቀጠለ"
ተቀፈቀፈ	"ቀፈቀፈ"
ተቁለጨለጨ	-"*ቁለጨ"
ተቁላላ	-"ቁላ^{1}"
ተቁነጠነጠ	-"*ቁነጠነጠ"
ተቃለለ	-"ቀለለ"
ተቃለደ	-"ቀለደ"
ተቃለጠ	-"ቀለጠ"
ተቃላጅ	-"ቀለደ"
ተቃመሰ	-"ቀመሰ"
ተቃማ	-"ቀማ"

ተቃረበ	-"ቀረበ"
ተቃረነ	"*ቀረነ"
ተቃረጠ	"ቀረጠ"
ተቃራኒ	-"*ቀረነ"
ተቃቃረ	-"*ቃቃረ"
ተቃበጠ	-"ቀበጠ"
ተቃና	-"ቀና^{2}"
ተቃወመ	-"*ቀወመ"
ተቃዋሚ	-"*ቀወመ"
ተቃወሰ	-"ቀወሰ"
ተቃጠለ	-"*ቃጠለ"
ተቃጣ	-"ቃጣ"
ተቃጨለ	-"ቃጨለ"
ተቅለሰለሰ	-"ቀለሰ"
ተቅለበለበ	-"*ቀለበለበ"
ተቅለጠለጠ	-"ቀለጠ"
ተቅመደመደ	-"*ቀመደመደ"
ተቅረፈረፈ	"ቀረፈ"
ተቅበዘበዘ	-"ቃበዘ"
ተቅበጠበጠ	"ቀበጠ"
ተቅነዘነዘ	-"*ቀነዘነዘ"
ተቅዘመዘመ	-"*ቀዘመዘመ
ተቅጨለጨለ	-"ቃጨለ"
ተቆለቆለ	-"ቆለቆለ"
ተቆለፈ	"ቆለፈ"
ተቆላ	-"ቆላ^{1}"
ተቆላለፈ	-"ቆለፈ"
ተቆላመመ	"ቆለመመ"
ተቆላመጠ	-"ቆለመጠ"
ተቆልማሚ	-"ቆለመመ"
ተቆመ	-"ቆመ"
ተቆመጠ	-"ቆመጠ"
ተቆማመጠ	-"ቆመጠ"
ተቆረሰ	-"ቆረሰ"
ተቆረበ	-"ቆረበ"
ተቆረቆረ	-"ቆረቆረ"
ተቆረጠ	-"ቆረጠ"
ተቆረማመደ	-"ቆረመደ"
ተቆራመደ	-"*ቆረመደ"
ተቆራረጠ	"ቆረጠ"
ተቆራቆሰ	-"ቆረቆሰ^{1}"
ተቆራኘ	-"*ቆረኘ"
ተቆራጭ	-"ቆረጠ"
ተቆራፈደ	-"ቆረፈደ"
ተቆርቋሪ	-"ቆረቆረ"
ተቆሳሰለ	"ቆሰለ"
ተቆሳቆሰ	-"ቆሰቆሰ"
ተቆታቸ	-"*ቆቲቸ"
ተቆነነ^{1}	-"ቆነነ^{2}"
ተቆነነ^{2}	-"ቆነነ^{3}"
ተቆነጃጀ	-"ቆነጀ"

ተቆንጠጠ	-"ቆንጠጠ"
ተቆናቆን	"ቆንቆን^2"
ተቆናጠረ	-"*ቆንጠረ"
ተቆናጠጠ	-"ቆንጠጠ"
ተቆዘረ	-"ቆዘረ"
ተቆጠረ	-"ቆጠረ"
ተቆጠበ	-"ቆጠበ"
ተቆጣ	-"*ቆጣ"
ተቆጣጠረ^1	-"ቆጠረ"
ተቆጣጠረ^2	-"ቋጠረ"
ተቆጣጣ	-"*ቆጣ"
ተቆጣጣሪ	-"ቆጠረ"
ተቆጨ	-"ቆጨ"
ተቆጭ	"*ቆጣ"
ተቆፈረ	-"ቆፈረ"
ተቆፋፈረ	-"ቆፈረ"
ተቋረሰ	-"ቆረሰ"
ተቋረጠ	-"ቆረጠ"
ተቋራጭ	"ቆረጠ"
ተቋሰለ	-"ቆሰለ"
ተቋቋመ	-"ቆመ"
ተቋደሰ	"*ቆደሰ"
ተቋጠረ^1	"ቆጠረ"
ተቋጠረ^2	-"ቋጠረ"
ተቋፈ	-"*ቋፈ^2"

ተበ

ተበለሻሸ	-"*በለሸ"
ተበለጠ	-"በለጠ^1"
ተበለጠጠ	-"በለጠጠ"
ተበላ	-"በላ"
ተበላለጠ	-"በለጠ^1"
ተበላሸ	-"*በለሸ"
ተበረቀሰ	-"በረቀሰ"
ተበረታታ	-"በረታ"
ተበረከተ	-"በረከተ"
ተበረዘ	-"በረዘ"
ተበረገደ	-"በረገደ"
ተበራታ	-"በረታ"
ተበራከተ	"በረከተ"
ተበራየ	-"*በረየ"
ተበራገደ	-"በረገደ"
ተበራገገ	-"በረገገ"
ተበሰረ	"*በሰረ"
ተበሰበሰ	-"በሰበሰ"
ተበሰከ	-"በሰከ"
ተበሳ	-"በሳ"
ተበሳሰከ	-"በሰከ"
ተበሳቆለ	-"በሰቆለ"
ተበሳበሰ	"በሰበሰ"
ተበሳጨ	-"* በሰጨ"
ተበሸረከ	-"በሸረከ"
ተበሸተ	-"በሸተ"
ተበሻቀጠ	-"በሸቀጠ"
ተበቀለ	-"በቀለ"
ተበተነ	-"በተነ"
ተበታተነ	-"በተነ"
ተበከለ	-"በከለ"
ተበከረች	-"*በከረ"
ተበዝባዥ	"በዘበዘ"
ተበደረ	-"*በደረ"
ተበደረገ	-"*በደረገ"
ተበዳሪ	-"*በደረ"
ተበጀ	-"በጀ^2"
ተበጃጀ	-"በጀ^2"
ተበጠረ^1	-"*በጠረ^1"
ተበጠረ^2	-"*በጠረ^2"
ተበጠሰ	-"በጠሰ"
ተበጠበጠ	-"በጠበጠ"
ተበጣሸ	-"በጠሰ"
ተበጣበጠ	-"በጠበጠ"
ተበጣጠሰ	"በጠሰ"
ተበጣጠቀ	-"በጠቀ"
ተበጫጨቀ	-"በጨቀ"
ተባለጠ	-"በለጠ^1"
ተባለጥ	-"በለጠ^1"
ተባሳ	-"በሳ"
ተባረረ	-"በረረ
ተባረከ	-"ባረከ"
ተባረዘ	-"በረዘ"
ተባረደ	-"በረደ"
ተባራሪ	-"በረረ"
ተባሰለ	-"በሰለ"
ተባቃ	-"በቃ"
ተባበረ	-"አበረ"
ተባባሪ	-"አበረ"
ተባበሰ	-"አበሰ"
ተባቢሰ	-"ባሰ"
ተባነነ	-"በነነ"
ተባቢለ	-"*ባበለ"
ተባዛ	-"በዛ"
ተባደለ	-"በደለ"
ተቤዠ	-"ቤዠ"
ተብለጠለጠ	-"በለጠ^2"
ተብለጨለጨ	-"*በለጨ"
ተብሳሳ	-"ፀሳ"
ተብረቀረቀ	-"በረቀ"
ተብረከረከ	-"በረከ"
ተብረጀረጀ	-"*በረጀረጀ"

ተብራራ	"በራ"
ተብሰከሰከ	"በሰከ"
ተቢቃቃ	-"ቢቃ"
ተብትከተከ	"በተከ"
ተብከነከነ	-"በከነ"
ተብጠለጠለ	-"*በጠለጠለ"
ተብጠሰጠሰ	-"በጠሰ"
ተቦረሸ	"ቦረሸ"
ተቦረቦረ	"ቦረቦረ"
ተቦተረፈ	"ቦተረፈ"
ተቦደሰ	-"ቦደሰ"
ተቦጠለቀ	"*ቦጠለቀ"
ተቦጫቀ	"ቦጫቀ"
ተቦጫጨቀ	"ቦጨቀ"
ተቧደነ	-"ቧደነ"
ተቧጨረ	"ቧጨረ"

ተተ

ተተለመ	-"ተለመ"
ተተረማመሰ	"*ተራመሰ"
ተተረተ	-"ተረተ"
ተተረተረ	"ተረተረ"
ተተረጎመ	-"ተረጎመ"
ተተራመሰ	"*ተራመሰ"
ተተበተበ	-"ተበተበ"
ተተቸ	-"ተቸ"
ተተነበየ	-"ተነበየ"
ተተናኮለ	-"ተነኮለ"
ተተናኮሰ	-"ተነኮሰ"
ተተከለ	-"ተከለ"
ተተኪ	-"ተካ"
ተተካ	-"ተካ"
ተተካይ	-"ተከለ"
ተተኮሰ	-"ተኮሰ"
ተተወ	"ተወ"
ተተገ^1	-"ተገተገ^1"
ተተፈተፈ	-"ተፈተፈ"
ተተፋ	"ተፋ"
ተታሰለ	-"*ታሰለ"
ተትመሰመሰ	-"* ረመሰመሰ"
ተትረፈረፈ	-"ተረፈ"
ተትከነከነ	"ተከነ"

ተቸ

ተቸመቸመ	-"ቸመቸመ"
ተቸረቸፈ	-"ቸረቸፈ"
ተቸበቸበ	"ቸበቸበ"
ተቸነከረ	-"ቸነከረ"
ተቸከለ	-"ቸከለ"
ተቸከቸከ	-"ቸከቸከ"
ተቸገረ	-"ቸገረ"
ተቻለ	-"ቻለ"
ተቻቻለ	-"ቻለ"
ተቻኮለ	-"ቸኮለ"

ተነ

ተንሿለለ	-"ንሆለለ"
ተንሰነሰ	"ነሰነሰ"
ተነሳ	-"*ነሳ"
ተነሳሳ	-"*ነሳ"
ተነሳው	"ነሳ"
ተነበበ	-"*ነበበ"
ተነባዘ	-"ነበዘ"
ተነባረረ	-"ነበረረ"
ተነባበረ	-"*ነበረበረ"
ተነባቢ	-"*ነበበ"
ተንቃነቀ	-"ነቀነቀ"
ተነከረ	-"ነከረ"
ተነከሰ	-"ነከሰ"
ተነካ	-"ነካ"
ተነካነከ	-"*ነከነከ"
ተነኳኳ	-"ነካ"
ተነዛነዘ	-"ነዘነዘ"
ተነዛናኸረ	-"ነዘነዘ"
ተነደለ	"ነደለ"
ተነደፈ	-"ነደፈ^1"
ተነዳ	-"ነዳ"
ተነዳደለ	"ነደለ"
ተነገረ	-"ነገረ"
ተነገነገ	-"ነገነገ^1"
ተንጋገረ	-"ነገረ"
ተንጎተ	-"*ንጎተ"
ተነጠለ	-"ነጠለ"
ተነጠፈ	"*ነጠፈ"
ተነጣጠረ	"*ነጠረ"
ተነጣጣሪ	"*ነጠረ"
ተነጫ	"ነጫ"
ተነጫነጨ	-"*ነጨነጨ"
ተነፃፀረ	-"*ነፀረ"
ተነፋ	-"ነፋ^1"
ተንፋለለ	-"ንፋለለ"

ተነፋረቀ "ነፈረቀ"

ተነፋነፈ	-"* ነፈነፈ^{1}"
ተናቀ	-"ናቀ"
ተናቆረ	"*ነቆረ"
ተናበበ	"*ነበበ"
ተናባቢ	"*ነበበ"
ተናነቀ	-"አነቀ"
ተናኘ	"ናኘ"
ተናከሸ	-"ነከሰ"
ተናወጠ	"*ነወጠ"
ተናዘዘ	-"ናዘዘ"
ተናደ	"ናደ"
ተናደደ	-"ነደደ^{2}"
ተናደፈ	-"ነደፈ^{1}"
ተናዷጀ	"ነደደ^{2}"
ተናዳፊ	"ነደፈ^{1}"
ተናገረ	-"ነገረ"
ተናጋ	-"*ነጋ"
ተናጋሪ	"ነገረ"
ተናጠ	-"ናጠ"
ተናጠላ	-"ነጠለ"
ተናጠል	-"ነጠለ"
ተናጠቀ	"ነጠቀ"
ተናጠበ	-"ነጠበ"
ተናፈረ	-"ነፈረ"
ተናፈሰ	"ነፈሰ"
ተናፈቀ	-"ናፈቀ"
ተናፈጠ	-"* ነፈጠ"
ተናፋቂ	-"ናፈቀ"
ተንሰለጀጀ	-"*ሰለጀጀ"
ተንሰቀሰቀ	-"*ሰቀሰቀ"
ተንሰፈሰፈ	-"*ሰፈሰፈ"
ተንሳፈፈ	-"ሰፈፈ"
ተንሶለሶለ	-"*ሶለሶለ"
ተንሸረሸረ	-"*ሸረሸረ"
ተንሸራሸረ	-"*ሸረሸረ"
ተንሸራተተ	-"*ሸረተተ"
ተንሸቀሸቀ	"ሸቀሸቀ^{2}"
ተንሸዋረረ	"ሸወረረ"
ተንሻረረ	-"*ሸረረ"
ተንሻተተ	-"ሻተተ"
ተንሻፈፈ	"ሸፈፈ"
ተንሾካሾከ	-"ሹክ"
ተንቀለቀለ	-"*ቀለቀለ"
ተንቀላበሰ	-"*ቀለበሰ"
ተንቀለጠጠ	-"*ቀለጠጠ"
ተንቀረቀበ	-"*ቀረቀበ"
ተንቀረበበ	-"*ቀረበበ"
ተንቀረደደ	-"ቀረደደ"
ተንቀረፈፈ	-"*ቀረፈፈ"

ተንቀራፈፈ	-"*ቀረፈፈ"
ተንቀሳቀሰ	"*ቀሰቀሰ"
ተንቀሳቃሽ	"*ቀሰቀሰ"
ተንቀሸረረ	-"ቀሸረረ"
ተንቀበቀበ	-"*ቀበቀበ"
ተንቀበደደ	-"ቀበደደ"
ተንቀባረረ	-"*ቀበረረ"
ተንቀወቀወ	-"*ቀወቀወ"
ተንቀዋለለ	-"*ቀወለለ"
ተንቀዠቀዠ	"*ቀዠቀዠ"
ተንቀጠቀጠ	"*ቀጠቀጠ"
ተንቀጧቀጨ	-"ቀጨቀጨ"
ተንቀፈረረ	-"*ቀፈረረ"
ተንቀፈደደ^{1}	-"ቀፈደደ"
ተንቀፈደደ^{2}	-"*ቀፈደደ"
ተንቃቃ	-"ቃ"
ተንቆረሰሰ	-"*ቆረሰሰ"
ተንቆረቆረ	-"* ቆረቆረ"
ተንቆረበበ	-"* ቆረበበ"
ተንቆረዘዘ	-"* ቆረዘዘ"
ተንቆረፈፈ	-"* ቆረፈፈ"
ተንቆራባ	-"ቆረባ"
ተንቆራጠጠ	-"*ቆረጠጠ"
ተንቆሻቆሸ	-"ቆሸቆሸ"
ተንቆሻበለ	-"* ቆሸበለ"
ተንቆጠቆጠ	-"*ቆጠቆጠ^{2}"
ተንቆጣቆጠ	-"*ቆጠቆጠ^{1}"
ተንቆጧቆጨ	"*ቆጨቆጨ"
ተንቋሸሸ	"ቆሸሸ"
ተንበለበለ	-"*በለበለ"
ተንበለጠጠ	-"በለጠጠ"
ተንበላጠጠ	"በለጠጠ"
ተንበረከከ	-"*በረከከ"
ተንበሸበሸ	-"*በሸበሸ"
ተንበከበከ	-"*በከበከ"
ተንበዛበዘ	-"*በዘበዘ"
ተንበደበደ	-"* በደበደ"
ተንበጣረረ	-"*በጠረረ"
ተንበጫበጨ	-"*በጨበጨ"
ተንቦለቦለ	-"* ቦለቦለ"
ተንቦረቀቀ	-"* ቦረቀቀ"
ተንቦቀቦቀ	-"* ቦቀቦቀ"
ተንቦዠቦዠ	"* ቦዠቦዠ"
ተንቦገቦገ	-"*ቦገቦገ"
ተንቦጫረቀ	-"*ቦጨረቀ"
ተንቦጫቦጨ	-"*ቦጨቦጨ"
ተንቧለለ^{1}	-"ቦለለ^{1}"
ተንቧለለ^{2}	-"ቦለለ^{2}"
ተንቧቧ	"*ቧቧ"
ተንቧቸ	-"*ቧቸ"

ተንተረከከ	-"ተረከከ"
ተንተረፈፈ	-"*ተረፈፈ"
ተንተራሰ	"*ተራሰ"
ተንተሰተሰ	"*ተሰተሰ"
ተንተበተበ	-"*ተበተበ^{2}"
ተንተባተበ	-"*ተበተበ^{1}"
ተንተከተከ	-"*ተከተከ"
ተንተገተገ	-"ተገተገ^{1}"
ተንታታ	"ታታ^{2}"
ተንቶሰቶሰ	-"*ቶሰቶሰ"
ተንቷቷ	-"ቷ^{2}"
ተንቸረፈፈ	-"*ቸረፈፈ"
ተንቸከቸከ	"*ቸከቸከ"
ተንቸፈረረ	"*ቸፈረረ"
ተንቻረረ	-"*ቸረረ"
ተንቻቻ	"ቻቻ"
ተንከሳወሰ	-"*ከሰወሰ"
ተንከረባበተ	-"ከረበተ"
ተንከረፈፈ	-"*ከረፈፈ"
ተንከረተተ	-"*ከረተተ"
ተንከራተተ	-"*ከረተተ"
ተንከባለለ	-"*ከበለለ"
ተንከባከበ	-"ከበከበ"
ተንከተከተ	-"*ኩተከተ"
ተንከወከወ	-"*ከወከወ"
ተንከዋተተ	-"*ከወተተ"
ተንከፈረረ	"ከፈረረ"
ተንኳኳ	-"*ኳኳ"
ተንኮሻኮሸ	-"ኮሸ"
ተንኮፈኮፈ	"*ኮፈኮፈ"
ተንኳለለ	"*ኮለለ^{1}"
ተንኳሸ	-"ተንኮሰ"
ተንኳተተ	"*ኩተተ"
ተንኳኳ	-"ኳ^{2}"
ተንዘለዘለ	-"ዘለዘለ"
ተንዘላዘለ	"ዘለዘለ"
ተንዘረበበ	"*ዘረበበ"
ተንዘረዘረ	"*ዘረዘረ"
ተንዘረጠጠ	-"ዘረጠጠ"
ተንዘረፈፈ	"*ዘረፈፈ"
ተንዘራጋ	"ዘረጋ"
ተንዘራፈጠ	"*ዘረፈጠ"
ተንዘፈዘፈ	"*ዘፈዘፈ"
ተንዘፈጠጠ	-"*ዘፈጠጠ"
ተንዛዛ	"*ዛዛ"
ተንዛፈፈ	"ዘፈፈ"
ተንዠረገገ	"*ዠረገገ"
ተንዠቀዠቀ	"*ዠቀዠቀ"
ተንዠባረረ	"*ዠበረረ"

ተንዠዋለለ	"*ዠወለለ"
ተንደላቀቀ	-"*ደለቀቀ"
ተንደረደረ	-"ደረደረ"
ተንደረበበ	-"*ደረበበ"
ተንደረከከ	-"*ደረከከ"
ተንደቀደቀ	"*ደቀደቀ"
ተንደበሰሰ	-"*ደበሰሰ"
ተንደበዘዘ	-"*ደበዘዘ"
ተንደበደበ	-"*ደበደበ"
ተንደባለለ	-"ደበለለ^{1}"
ተንደከደከ	-"*ደከደከ"
ተንደፋደፈ	"*ደፈደፈ"
ተንዳሰሰ	-"*ዳሰሰ"
ተንዳኮኮ	-"ዶኮኮ"
ተንዶለዶለ	"*ዶለዶለ"
ተንደሸደሸ	"*ደሸደሸ"
ተንጀለጀለ	-"*ጀለጀለ"
ተንጀላጀለ	"*ጀለጀለ"
ተንገለጠጠ	-"ገለጠጠ"
ተንገላታ	"*ገለታ"
ተንገላጀጀ	"*ገለጀጀ"
ተንገረበበ	"*ገረበበ"
ተንገረገበ	-"*ገረገበ"
ተንገሸገሸ	-"*ገሸገሸ"
ተንገበገበ	-"*ገበገበ"
ተንገታገተ	-"*ገተገተ"
ተንገቸገቸ	"*ገቸገቸ"
ተንገዋለለ	-"*ገወለለ"
ተንገደገደ	"*ገደገደ"
ተንገዳገደ	"*ገደገደ"
ተንገዘገዘ	-"*ገዘገዘ"
ተንገጫገጨ	-"*ገጨገጨ"
ተንገፈጠጠ	"*ገፈጠጠ"
ተንገፈገፈ	-"*ገፈገፈ"
ተንጋለለ	"*ጋለለ"
ተንጋተተ	"ገተተ"
ተንጋደደ	"ገደደ^{1}"
ተንጋጋ	-"*ጋጋ"
ተንጋጠጠ	-"*ገጠጠ"
ተንጎራደደ	-"*ጎረደደ"
ተንጎደጎደ	-"*ጎደጎደ"
ተንጎዳጎደ	"ጉድ"
ተንጎፈጠጠ	-"ጎፈጠጠ"
ተንጓበበ	"ጎበበ"
ተንጓደደ	-"*ጎደደ"
ተንጓጓ	-"ጓ^{2}"
ተንጓጠጠ	-"ጓጠጠ"
ተንጓፈፈ	-"*ጎፈፈ"
ተንጠለጠለ	"*ጠለጠለ"
ተንጠላጠለ	"*ጠለጠለ"

ተንጠረበበ	-"*ጠረበበ"
ተንጠረዘዘ	"*ጠረዘዘ"
ተንጠረጠረ	"ጠረጠረ^{2}"
ተንጠራራ	-"*ጠራራ"
ተንጠራወዘ^{1}	-"*ጠረወዘ"
ተንጠራወዘ^{2}	"*ጠራወዘ"
ተንጠበጠበ	-"*ነጠበ"
ተንጠባረረ	"*ጠበረረ"
ተንጠባጠበ^{1}	-"ነጠበ"
ተንጠባጠበ^{2}	-"ጠገ"
ተንጠፈጠፈ	-"*ጠፈጠፈ"
ተንጣለለ	"*ጠለለ^{1}"
ተንጣጣ	"*ጣጣ"
ተንጦለጦለ	-"*ጦለጦለ"
ተንጦሸጦሸ	-"ጦሸ"
ተንጦዘጦዘ	-"*ጦዘጦዘ"
ተንጧጧ	-"ጧ^{2}"
ተንጨረገገ	"*ጨረገገ"
ተንጨረጨረ	"*ጨረጨረ"
ተንጨረፈፈ	-"*ጨረፈፈ"
ተንጨበረረ	-"*ጨበረረ"
ተንጨፈረረ	-"ጨፈረረ"
ተንጫረረ	"*ጨረረ^{1}"
ተንጫጫ	-"*ጫጫ"
ተንፀበረቀ	-"*ፀበረቀ"
ተንፈሳሰሰ	-"*ፈሰሰሰ"
ተንፈረዘዘ	-"*ፈረዘዘ"
ተንፈራከከ	-"*ፈረከከ"
ተንፈራገጠ	-"*ፈረገጠ"
ተንፈራጠጠ	"*ፈረጠጠ"
ተንፈራፈረ	"*ፈረፈረ"
ተንፈቀፈቀ	"*ፈቀፈቀ"
ተንፈጨፈጨ	-"*ፈጨፈጨ"
ተንፎለፎለ	-"*ፎለፎለ"
ተንፎሸፎሸ	-"*ፎሸፎሸ"
ተንፎደፎደ	-"ፎደፎደ"
ተንፏቀቀ	-"*ፏቀቀ^{1}"
ተንፏፏ	-"*ፏፏ"

ተከ

ተከለለ	"ከለለ^{1}"
ተከለከለ	"ከለከለ"
ተከላከለ	"ከለከለ"
ተከላካይ	-"ከለከለ"
ተከመረ	"ከመረ"
ተከማቸ	"*ከመቸ"
ተከረቸመ	-"ከረቸመ"
ተከረከረ	-"ከረከረ"
ተከራረመ	-"ከረመ"
ተከራከረ	-"*ከረከረ"
ተከራየ	"*ከረየ"
ተከራይ	"*ከረየ"
ተከርቸም	-"ከረቸመ"
ተከሰከሰ	-"ከሰሰ"
ተከሰተ	-"ከሰተ"
ተከሰከሰ	-"ከሰከሰ"
ተከሳሽ	-"ከሰሰ"
ተከሳከሰ	-"ከሰከሰ"
ተከበረ	-"ከበረ"
ተከባከበ	-"ከበከበ"
ተከተለ	-"*ከተለ"
ተከተበ	"ከተበ"
ተከተተ	-"ከተተ"
ተከታለበ	-"*ከተለበ"
ተከታተለ	-"*ከተለ"
ተከታተመ	"ከተመ^{1}"
ተከታታይ	-"*ከተለ"
ተከታይ	-"*ከተለ"
ተከነቸረ	-"ከነቸረ"
ተከናነበ	-"*ከነበ"
ተከናወነ	-"*ከነወነ"
ተከፋ	"ከፋ"
ተከፋች	-"ከፈተ"
ተከፋፈለ	-"ከፈለ"
ተኩረፈረፈ	"ኩረፈ"
ተኩነሰነሰ	-"*ኮንሰነሰ"
ተኩራራ	-"ኮራ^{1}"
ተካለለ	"ከለለ^{1}"
ተካለበ	-"ከለበ"
ተካረመ	-"ከረመ"
ተካረረ	"ከረረ"
ተካሰ	-"ካሰ"
ተካሰሰ	-"ከሰሰ"
ተካበደ	"ከበደ"
ተካተተ	"ከተተ"
ተካነ	-"ካነ"
ተካከለ	-"አከለ"
ተካካሰ	-"ካሰ"
ተካይ	-"ተከለ"
ተካፈለ	-"ከፈለ"
ተካፋች	-"ከፈተ"
ተካፋይ	-"ከፈለ"
ተኮለበለበ	-"ከለበ"
ተኮለፈለፈ	"*ከለፈ"
ተኮበሰበሰ	-"*ከበሰበሰ"
ተኮተፈተፈ	-"*ኮተፈ"
ተኮነፈነፈ	-"ኮነፈ"
ተኮለኮለ	-"ኮለኮለ^{1}"

ተኮለታተፈ	-"*ኮለተፈ"
ተኮላሸ	-"*ኮላሸ"
ተኮላተፈ	-"*ኮለተፈ"
ተኮረመተ	"ኮረመተ"
ተኮራረፈ	-"*ኮረፈ^1"
ተኮሳተረ	-"ኮሰተረ^2"
ተኮንተሸ	-"ኮንተሸ"
ተኮናተረ	-"*ኮናተረ"
ተኮፈሰ	"ኮፈሰ"
ተኮፋንን	-"*ኮፈንን"
ተኳለ	-"ኳለ"
ተኳረፈ	-"*ኮረፈ^1"
ተኳሰ	-"*ኳሰ"
ተኳኳለ	-"ኳለ"

ተወ

ተወለካከፈ	-"ወለከፈ"
ተወለወለ	-"ወለወለ"
ተወለደ	-"ወለደ"
ተወለጋገደ	-"ወለገደ"
ተወላመመ	-"*ወለመመ"
ተወላመጠ	-"*ወለመጠ"
ተወላከፈ	-"ወለከፈ"
ተወላጻ	-"*ወላጻ"
ተወላጀ	"ወለደ"
ተወላገመ	-"ወለገመ"
ተወላገደ	"ወለገደ"
ተወረረ	-"ወረረ"
ተወረሰ	-"ወረሰ"
ተወረወረ	"ወረወረ"
ተወረደ	-"ወረደ"
ተወራ	"*ወራ"
ተወራረሰ	-"ወረሰ"
ተወራረደ	-"ወረደ"
ተወራራሸ	"ወረሰ"
ተወራወረ	-"ወረወረ"
ተወራጀ	-"ወረደ"
ተወራጨ	-"*ወረጨ"
ተወሰነ	"ወሰነ"
ተወሰወሰ	-"ወሰወሰ"
ተወሰደ	-"ወሰደ"
ተወሳ	-"*ወሳ"
ተወሳሰበ	-"*ወሰበሰበ"
ተወሸመ	"ወሸመ"
ተወሸቀ	-"ወሸቀ"
ተወሻከተ	-"ወሸከተ"
ተወሻገረ	-"ወሸገረ"
ተወቀረ	-"ወቀረ"
ተወቀሰ	"ወቀሰ"
ተወቀጠ	-"ወቀጠ"
ተወቃ	-"ወቃ"
ተወቃሸ	-"ወቀሰ"
ተወባራ	"ወበራ^2"
ተወተፈ	-"ወተፈ"
ተወታተፈ	-"ወተፈ"
ተወናባበደ	"ወነበደ"
ተወነጀለ	-"ወነጀለ"
ተወነገ	-"ወነገ"
ተወነጠ	-"*ወነጠ"
ተወነጨፈ	"ወነጨፈ"
ተወናበደ	-"ወነበደ"
ተወናከረ	-"*ወነከረ"
ተወናወነ	-"*ወነወነ"
ተወናጨፈ	-"ወነጨፈ"
ተወናፈለ	"*ወነፈለ"
ተወከለ	-"ወከለ"
ተወካይ	-"ወከለ"
ተወዘተ	-"ወዘተ"
ተወዘወዘ	"ወዘወዘ"
ተወዘፈ	-"ወዘፈ"
ተወዛወዘ	-"ወዘወዘ"
ተወዛዋዥ	"ወዘወዘ"
ተወዛዛ	-"ወዛ"
ተወዛገበ	-"*ወዛገበ"
ተወደረ	-"ወደረ"
ተወደሰ	"*ወደሰ"
ተወደነ	-"ወደነ"
ተወደደ	-"ወደደ"
ተወዳደረ	-"*ወደረ"
ተወዳዳሪ	-"*ወደረ"
ተወዳጀ	-"ወደደ"
ተወገዘ	-"*ወገዘ"
ተወገደ	-"*ወገደ"
ተወጋ	-"ወጋ "
ተወጠረ	-"ወጠረ"
ተወጠነ	-"ወጠነ"
ተወጣ	"ወጣ" *
ተወጣጠረ	-"ወጠረ"
ተዋሃደ	-"*ዋሃደ"
ተዋለደ	"ወለደ"
ተዋረደ	"ወረደ"
ተዋረድ	-"ወረደ"
ተዋሰ^1	"*ዋሰ^1"
ተዋሰ^2	"*ዋሰ^2"
ተዋሳኝ	-"ወሰነ"
ተዋቃ	-"ወቃ"
ተዋበ	-"*ዋበ "
ተዋከበ	-"*ወከበ"
ተዋወቀ	-"ወቀ"

ተዋዋለ	"ዋለ^{2}"
ተዋዛ	-"*ዋዛ"
ተዋደቀ	-"ወደቀ"
ተዋደደ	-"ወደደ"
ተዋጋ	-"ወጋ"
ተዋጣ	-"ወጣ"
ተውለበለበ	"*ወለበ"
ተውረገረገ	-"*ወረገረገ"
ተውሸለሸለ	-"ወሸለ"
ተውተረተረ	-"*ወተረ"
ተውተበተበ	-"*ወተበተበ"
ተውተፈተፈ	-"ወተፈ"
ተውጣጣ	"ወጣ"

ተዘ

ተዘለለ^{1}	-"ዘለለ^{1}"
ተዘለለ^{2}	-"ዘለለ^{2}"
ተዘለቀ	-"ዘለቀ"
ተዘመዘመ	-"ዘመዘመ"
ተዘረረ	"ዘረረ"
ተዘረከተ	-"ዘረከተ"
ተዘረዘረ	-"ዘረዘረ"
ተዘረገፈ	-"ዘረገፈ"
ተዘረጋ	-"ዘረጋ"
ተዘረጋጋ	-"ዘረጋ"
ተዘረጠጠ	-"ዘረጠጠ"
ተዘረፈ	"ዘረፈ"
ተዘረፈጠ	-"*ዘረፈጠ"
ተዘራ	-"ዘራ"
ተዘራዘረ	-"ዘረዘረ"
ተዘቀዘቀ	"ዘቀዘቀ"
ተዘበራረቀ	-"ዘባረቀ"
ተዘበጠ	-"ዘበጠ"
ተዘባረቀ	"ዘባረቀ"
ተዘባበተ	-"ዘበተ"
ተዘባነነ	-"*ዘበነነ"
ተዘነቀ	-"ዘነቀ"
ተዘነተረ	-"ዘነተረ"
ተዘነጋ	-"ዘነጋ"
ተዘነጠለ	-"ዘነጠለ"
ተዘነጠፈ	-"ዘነጠፈ"
ተዘናከተ	"*ዘነከተ"
ተዘናዘነ	-"ዘነዘነ"
ተዘናጋ	-"ዘነጋ"
ተዘናፈለ	"*ዘነፈለ"
ተዘከረ	-"ዘከረ"
ተዘወተረ	"*ዘወተረ"
ተዘዋወረ	-"ዞረ"
ተዘዋዋሪ	-"ዞረ"
ተዘየነ	-"ዘየነ"
ተዘገነ	-"ዘገነ"
ተዘገጃጀ	-"*ዘገጀ"
ተዘጋ	-"ዘጋ"
ተዘጋጀ	"*ዘገጀ"
ተዘጠረ	-"ዘጠረ"
ተዘፈቀ	-"ዘፈቀ"
ተዛለለ	-"ዘለለ^{1}"
ተዛለቀ	-"ዘለቀ"
ተዛመተ	-"ዘመተ"
ተዛመደ	"*ዘመደ"
ተዛረፈ	"*ዘረፈ"
ተዛቀ	-"ዛቀ"
ተዛባ	-"ዘባ"
ተዘነቀ	-"ዘነቀ"
ተዛነፈ	"*ዘነፈ"
ተዛነፍ	-"*ዘነፈ"
ተዛና	-"ዘና"
ተዛወረ	-"ዞረ"
ተዛዘለ	"እዘለ "
ተዛዛበ	-"ታዘበ"
ተዛዘነ	-"አዘነ"
ተዝለገለገ	-"*ዘለገለገ"
ተዝለፈለፈ	-"*ዘለፈለፈ"
ተዝረበረበ	-"*ዘረበረበ"
ተዝረከረከ	-"*ዘረከረከ"
ተዝረጠረጠ	-"*ዘረጠ"
ተዝረፈረፈ	-"*ዘረፈ"
ተዝቦጠቦጠ	-"*ዘቦጠቦጠ"
ተዝናና	-"ዘና"
ተዝጎረጎረ	-"*ዥጎረጎረ"
ተዟዟረ	-"ዞረ"
ተዟዟሪ	-"ዞረ"

ተዠ

ተዥሞለሞለ	-"*ዥሞለሞለ"
ተዥጎረጎረ	-"*ዥጎረጎረ"

ተየ

ተያየ	-"አየ"

ተደ

ተደለለ	"ደለለ^{1}"
ተደለቀ^{1}	-"ደለቀ^{1}"
ተደለቀ^{2}	-"ደለቀ^{2}"
ተደለዘ	-"ደለዘ^{1}"
ተደላደለ	"ደለደለ"

ተደመለለ	-"ደመለለ"
ተደመመ	"*ደመመ"
ተደመሰሰ	-"ደመሰሰ"
ተደመጠ	"*ደመጠ"
ተደማመጠ	-"*ደመጠ"
ተደማጭ	-"*ደመጠ"
ተደረመሰ	-"ደረመሰ"
ተደረሰ	-"ደረሰ^{1}"
ተደረበ	-"ደረበ"
ተደረደረ	-"ደረደረ"
ተደረጃጀ	"ደረጀ"
ተደረገ	-"*ደረገ"
ተደረገመ	-"ደረገመ"
ተደራረበ	-"ደረበ"
ተደራራቢ	-"ደረበ"
ተደራራጊ	-"*ደረገ"
ተደራቢ	-"ደረበ"
ተደራደረ	-"ደረደረ"
ተደራዳሪ	-"ደረደረ"
ተደራጀ	-"ደረጀ"
ተደሰተ	"*ደሰተ"
ተደሳች	"*ደሰተ"
ተደቀለ	-"ደቀለ"
ተደቀነ	-"ደቀነ"
ተደቆሰ	-"ደቆሰ"
ተደበለለ	-"ደበለለ^{2}"
ተደበላለቀ	-"ደባለቀ"
ተደበረ	-"ደበረ^{3}"
ተደበቀ	-"ደበቀ"
ተደበደበ	-"ደበደበ^{1}"
ተደባለቀ	-"ደባለቀ"
ተደባበቀ	-"ደበቀ"
ተደባደበ	-"ደበደበ^{1}"
ተደባዳቢ	-"ደበደበ^{1}"
ተደነሰረ	-"*ደነሰረ"
ተደነቀ	-"ደነቀ"
ተደነቀረ	-"ደነቀረ"
ተደነቃቀፈ	-"*ደነቀፈ"
ተደነገገ	"ደነገገ"
ተደነጋገረ	-"*ደነገረ"
ተደነጓጎረ	-"ደነጎረ^{2}"
ተደናቀፈ	"*ደነቀፈ"
ተደናቂ	-"ደነቀ"
ተደናቆረ	-"ደነቆረ"
ተደናበረ	-"ደነበረ^{2}"
ተደናከረ	-"*ደነከረ"
ተደናገረ	-"*ደነገረ"
ተደናገጠ	-"ደነገጠ"
ተደናጎረ	-"ደነጎረ^{2}"
ተደከረ	"ደከረ"

ተደካ	"ደካ^{1}"
ተደወለ	-"ደወለ"
ተደወረ	-"ደወረ"
ተደገሰ	-"ደገሰ"
ተደገፈ	-"ደገፈ"
ተደጋገመ	"ደገመ^{1}"
ተደጋገፈ	-"ደገፈ"
ተደጋጋሚ	-"ደገመ^{1}"
ተደጋጋፊ	"ደገፈ"
ተደጎመ	-"ደጎመ"
ተደፈረ	-"ደፈረ"
ተደፈቀ	-"ደፈቀ"
ተደፈነ	-"ደፈነ"
ተደፈጠጠ	-"ደፈጠጠ"
ተደፋ	"ደፋ"
ተደፋፈረ	-"ደፈረ"
ተደፋፋ	-"ደፋ"
ተዳማ	"ደማ"
ተዳረሰ	-"ደረሰ^{1}"
ተዳረቀ	-"ደረቀ"
ተዳበለ	"ደበለ"
ተዳራ	-"*ደራ^{1}"
ተዳቀለ	-"ደቀለ"
ተዳቀቀ	-"ደቀቀ"
ተዳቆሰ	-"ደቆሰ"
ተዳረገ	-"ዳረገ"
ተዳነ	-"ዳነ"
ተዳኘ	-"ዳኘ"
ተዳከመ	-"ደከመ"
ተዳወለ	-"ደወለ"
ተዳወረ	-"ደወረ"
ተዳደረ	-"አደረ"
ተዳዳሪ	"አደረ^{1}"
ተዳፈነ^{1}	-"ደፈነ"
ተዳፈነ	-"* ዳፈነ^{2}"
ተዳፋ	-"ደፋ"
ተዶመነመነ	-"ዶመነ"
ተዶበለበለ	-"*ደበለበለ"
ተዶበሰበሰ	-"ደበሰ"
ተዶበከበከ	-"*ደበከበከ"
ተዶጎለጎለ	"*ደጎለጎለ"
ተዶፈነፈነ	-"ደፈነ"
ተዶፈጠፈጠ	-"*ደፈጠፈጠ"

ተጀ

ተጀመረ	-"ጀመረ"
ተጀቦነ	-"ጀቦነ"
ተጀነነ	-"ጀነነ"
ተጀነጀነ	"ጀነጀነ"
ተጃጃለ	"ጀለ"

ተገ

ተገለለ	"*ገለለ"
ተገለሰሰ	-"ገለሰሰ"
ተገለቢ^{1}	-"ገለበ^{1}"
ተገለበ^{2}	-"ገለበ^{2}"
ተገለባበጠ	-"ገለበጠ"
ተገለባባጭ	-"ገለበጠ"
ተገለደመ	-"*ገለደመ"
ተገለገለ	-"*ገለገለ"
ተገለጠ	"ገለጠ"
ተገለጠጠ	-"ገለጠጠ"
ተገለፈጠ	-"ገለፈጠ"
ተገለፈፈ	"ገለፈፈ"
ተገሳመጠ	-"ገሳመጠ"
ተገሳበጠ	-"ገለበጠ"
ተገሳወደ	"*ገለወደ"
ተገሳገለ	-"ገሳገለ"
ተገልጋይ	-"*ገለገለ"
ተገመለ	-"ገመለ"
ተገመተ	-"ገመተ"
ተገመጠ	-"ገመጠ^{2}"
ተገማመተ	-"ገመተ"
ተገማሸረ	-"*ገመሸረ"
ተገረመ	"ገረመ^{1}"
ተገረደች	-"ገረደ"
ተገራ	"ገራ^{1}"
ተገሰሰ	"ገሰሰ^{3}"
ተገሰፀ	-"ገሰፀ"
ተገሸለጠ	-"ገሸለጠ"
ተገሸላለጠ	-"ገሸለጠ"
ተገሸረ	-"ገሸረ^{1}"
ተገበዘ	-"*ገበዘ"
ተገበያየ	-"ገበየ"
ተገቢ	-"ገባ"
ተገባ	-"ገባ"
ተገባደደ	"*ገበደደ"
ተገተረ	-"ገተረ"
ተገታ	-"ገታ"
ተገነባ	"ገነባ"
ተገነዘበ	-"*ገነዘበ"
ተገነደሰ	-"ገነደሰ"
ተገነጠለ	-"ገነጠለ"
ተገነፈለ	-"ገነፈለ"
ተገነፋ	-"*ገነፋ"
ተገናኘ	-"*ገነኘ"
ተገንጣይ	-"ገነጠለ"
ተገኘ	-"*ገነኘ"
ተገዘተ	-"ገዘተ"
ተገዘገዘ	-"ገዘገዘ"
ተገዛ	-"ገዛ"
ተገደለ	-"ገደለ"
ተገደመ	-"ገደመ"
ተገደረ	-"*ገደረ"
ተገደበ	"ገደበ"
ተገደደ	-"ገደደ^{2}"
ተገደገደ	-"ገደገደ"
ተገደፈ	"ገደፈ^{1}"
ተገዳደመ	-"ገደመ"
ተገዳደረ	-"*ገደረ"
ተገጠገጠ	-"ገጠገጠ^{1}"
ተገጣጠመ	-"ገጠመ"
ተገጣጣሚ	-"ገጠመ"
ተገጨ	-"ገጨ"
ተገፋ	-"ገፋ"
ተገፋፋ	-"ገፋ"
ተጉረመረመ	-"*ጉረመረመ"
ተጉረበረበ	"ጉረበ"
ተጉረጠረጠ	-"ጉረጠ"
ተጊያጊያጠ	-"*ጊየጠ"
ተጋለጠ	-"ገለጠ"
ተጋረጠ	-"ጋረጠ"
ተጋራ	-"*ጋራ"
ተጋበዘ	"ጋበዘ"
ተጋባ	-"ጋባ"
ተጋባኝ	-"ጋበዘ"
ተጋተ	-"ጋተ"
ተጋተረ	-"ገተረ"
ተጋዘ^{1}	-"*ጋዘ^{1}"
ተጋዘ^{2}	-"*ጋዘ^{2}"
ተጋደለ	-"ገደለ"
ተጋደመ	"*ገደመ"
ተጋጻይ	-"ገደለ"
ተጋገዘ	-"አገዘ"
ተጋጋለ	-"ጋለ"
ተጋጋመ	-"ጋመ"
ተጋጋጠ	-"ጋጠ"
ተጋጠመ	-"ገጠመ"
ተጋጨ	-"ገጨ"
ተጋፈጠ	-"*ጋፈጠ"
ተጋፋ	-"ገፋ"
ተጌጠ	"*ጌየጠ"
ተግለሰለሰ	-"*ገለሰለሰ"
ተግለበለበ	-"*ገለበለበ"
ተግመነመነ	-"ገመነ"
ተግማማ	-"ገማ"
ተግበሰበሰ	"*ገበሰበሰ"
ተግባቢ	"ገባ"
ተግባባ	-"ገባ"
ተግተለተለ	-"*ገተለተለ"
ተግተረተረ	"ገተረ"
ተግደረደረ	-"*ገደረደረ"

ተግደርዳሪ	-"*ገደረደረ"
ተግፈለፈለ	-"*ገፈለፈለ"
ተጎለተ	-"ጎለተ"
ተጎለጎለ	-"ጎለጎለ"
ተጎሳደፈ	"ገለደፈ"
ተጎመረ	-"ጎመረ"
ተጎመተ	-"ጎመተ"
ተጎማለለ	-"*ጎመለለ"
ተጎራበተ	-"*ጎረበተ"
ተጎራባች	-"*ጎረበተ"
ተጎሰረ	-"ጎሰረ"
ተጎሳቆለ	-"ጎሰቆለ"
ተጎበረ	-"ጎበረ"
ተጎበጎበ	-"*ጎበጎበ"
ተጎተተ	"ጎተተ"
ተጎታች	-"ጎተተ"
ተጎነበሰ	-"*ጎነበሰ"
ተጎነጨ	-"*ጎነጨ"
ተጎናበሰ	-"*ጎነበሰ"
ተጎናዘለ	-"*ጎነዘለ"
ተጎናፀፈ	"*ጎነፀፈ"
ተጎዳ	-"ጎዳ"
ተጎዳኘ	-"*ጎደኘ"
ተጋመተ	-"ገመተ"
ተጓተተ	"ጎተተ"
ተጓዘ	-"*ጓዘ"
ተጓዥ	-"*ጓዘ"
ተጓደለ	-"ጎደለ"
ተጓደደ	-"*ጎደደ"
ተጓጎለ	"አጎለ"

ተጠ

ተጠሀነነ	-"ጠሀነነ"
ተጠለለ	"*ጠለለ^{2}"
ተጠለፈ	-"ጠለፈ"
ተጠሳ	-"ጠሳ^{2}"
ተጠሳሳፈ	-"ጠለፈ"
ተጠሳፈ	-"ጠለፈ"
ተጠመቀ	"ጠመቀ^{2}"
ተጠመዘዘ	"ጠመዘዘ"
ተጠመደ	-"ጠመደ^{1}"
ተጠመጠመ	"ጠመጠመ"
ተጠማ	-"ጠማ"
ተጠማዘዘ	-"ጠመዘዘ"
ተጠሞረ	"ጠሞረ"
ተጠረመሰ	"ጠረመሰ"
ተጠረቀ	-"ጠረቀ"
ተጠረቀመ	"ጠረቀመ"
ተጠረዘ	-"ጠረዘ"
ተጠረገ	-"ጠረገ"
ተጠረጠረ	-"ጠረጠረ^{1}"
ተጠሪ	"ጠራ^{1}"
ተጠራ	-"ጠራ^{1}"
ተጠራረገ	-"ጠረገ"
ተጠራራ	-"ጠራ^{1}"
ተጠራቀመ	-"*ጠረቀመ"
ተጠራጠረ	-"ጠረጠረ^{1}"
ተጠራጣሪ	"ጠረጠረ^{1}"
ተጠርጣሪ	-"ጠረጠረ^{1}"
ተጠቀመ	-"ጠቀመ^{1}"
ተጠቀጠቀ	-"ጠቀጠቀ^{1}"
ተጠቃ	-"*ጠቃ"
ተጠቃለለ	-"ጠቀለለ"
ተጠቃሚ	"ጠቀመ^{1}"
ተጠቃቀሰ	-"ጠቀሰ^{1}
ተጠቃች	-"ጠቃ"
ተጠቆመ	"ጠቆመ"
ተጠቆረ	"ጠቆረ"
ተጠቋሚ	-"ጠቆመ"
ተጠቋቆመ	-"ጠቆመ"
ተጠበሰ	"ጠበሰ"$_{1}$
ተጠበቀ^{1}	-"ጠበቀ^{1}
ተጠበቀ^{2}	-"ጠበቀ^{3}
ተጠበበ	"*ጠበበ"
ተጠባበቀ	-"ጠበቀ^{3}"
ተጠባባቂ	-"ጠበቀ^{3}"
ተጠነሰሰ	-"ጠነሰሰ^{1}"
ተጠነቀቀ	-"*ጠነቀቀ"
ተጠና	-"*ጠና"
ተጠናቀቀ	-"*ጠነቀቀ"
ተጠናበረ	-"*ጠነበረ"
ተጠናበሰ	-"ጠነበሰ"
ተጠናና	-"*ጠና"
ተጠናከረ	-"ጠነከረ"
ተጠዛጠዘ	-"ጠዘጠዘ"
ተጠየቀ	"ጠየቀ"
ተጠየቅ	-"ጠየቀ"
ተጠየፈ	-"*ፀየፈ""
ተጠያቂ	-"ጠየቀ"
ተጠያየቀ	-"ጠየቀ"
ተጠጋ	-"*ጠጋ"
ተጠጋጋ	-"*ጠጋ"
ተጠፋፋ	"ጠፋ^{1}"
ተጣለ	"ጣለ"$_{2}$
ተጣላ	-"ጠላ^{2}"
ተጣመመ	"ጠመመ"
ተጣመረ	-"*ጠመረ"
ተጣመደ	"ጠመደ^{1}"
ተጣማሪ	-"*ጠመረ"
ተጣረሰ	-"ጠረሰ"

ተጣራ^1	-"ጣራ^1"
ተጣራ^2	-"ጣራ^2"
ተጣሰ	-"ጣሰ"
ተጣቀሰ	-"ጠቀሰ"
ተጣበሰ	-"ጠበሰ"
ተጣበበ	"ጠበበ"
ተጣበቀ	-"*ጠበቀ^1"
ተጣደ	-"ጣደ"
ተጣደፈ	"*ጠደፈ"
ተጣገበ	-"ጠገበ"
ተጣጋ	-"*ጠጋ"
ተጣጠበ	-"አጠበ"
ተጣጠፈ	-"አጠፈ"
ተጣጣ^1	-"ጠጣ"
ተጣጣ^2	-"አጣ"
ተጣጣመ	-"ጣመ"
ተጣጣረ	-"ጣረ"
ተጣፈ	-"ጣፈ"
ተጣፋ^1	-"ጠፋ^1"
ተጣፋ^2	-"ጠፋ^2"
ተጤነ	-"*ጤነ"
ተጥለቀለቀ	-"ጠለቀ^3"
ተጥመዘመዘ^1	-"*ጠመዘመዘ"
ተጦረ	-"ጦረ/ጠመረ/"
ተጧሪ	-"ጧረ"
ተጧጧፈ	-"ጦፈ"

ተጨ

ተጨመረ	"ጨመረ"
ተጨመጨመ	-"ጨመጨመ^2"
ተጨማመረ	"ጨመረ"
ተጨማሪ	"ጨመረ"
ተጨማተረ	-"ጨምተረ"
ተጨራመመ	-"*ጨረመመ"
ተጨራመተ	-"ጨረመተ"
ተጨቃጨቀ	-"ጨቀጨቀ^1"
ተጨቃጫቂ	-"ጨቀጨቀ^1"
ተጨቆነ	-"ጨቆነ"
ተጨቋኝ	-"ጨቆነ"
ተጨበጠ	-"ጨበጠ"
ተጨበጨበ	-"*ጨበጨበ"
ተጨባበጠ	-"ጨበጠ"
ተጨነቀ	-"ጨነቀ"
ተጨናቆረ	-"ጨነቆረ"
ተጨናበሰ	-"*ጨነበሰ"
ተጨናነቀ	-"ጨነቀ"
ተጨናገፈ	-"ጨነገፈ"
ተጨናጎለ	-"*ጨነጎለ"
ተጨፈለቀ	-"ጨፈለቀ"
ተጨፈረ	-"ጨፈረ"
ተጨፈቀ	-"ጨፈቀ"
ተጨፈነ	-"ጨፈነ"
ተጨፈጨፈ	-"ጨፈጨፈ^1"
ተጫማ	-"*ጫማ"
ተጫረ	-"ጫረ"
ተጫረበ	-"ጨረበ"
ተጫረተ	-"*ጨረተ"
ተጫራች	-"*ጨረተ"
ተጫነ	"ጫነ"
ተጫወተ	-"*ጨወተ"
ተጫዋች	-"*ጨወተ"
ተጫጫረ	"ጫረ"
ተጫጫሰ	-"ጨሰ/ጤሰ/"
ተጫነ	-"ጫነ"
ተጫጫነ	-"ጫነ"
ተጯበረበረ	-"*ጨበረበረ"
ተጯበሰበሰ	-"*ጨበሰበሰ"
ተጯፈነፈነ	-"ጨፈነ"
ተጮሀ	-"ጮሀ"
ተጯጯሀ	-"ጮሀ"

ተፀ

ተፀየፈ	-"*ፀየፈ"
ተፀያፊ	-"*ፀየፈ"
ተፀዳዳ	-"ፀዳ/ጠዳ/"
ተፀፀተ	-"ፀፀተ/ጠጠተ/"
ተፃረረ	-"*ፀረረ"
ተፃራሪ	-"*ፀረረ"
ተፅናና	-"ጠና"

ተፈ

ተፈለቀቀ	-"ፈለቀቀ"
ተፈለሰፈ	-"ፈለሰፈ/ለሰመ/"
ተፈለገ	-"ፈለገ"
ተፈለፈለ	-"ፈለፈለ^2"
ተፈላለገ	-"ፈለገ"
ተፈላለጉ	"ፈለገ"
ተፈላሰፈ	-"ፈለሰፈ"
ተፈላፈ	-"ፈለሰፈ"
ተፈላጊ	"ፈለገ"
ተፈረመ	-"ፈረመ"
ተፈረቀቀ	-"ፈረቀቀ"
ተፈረነሰ	-"*ፈረነሰ"
ተፈረከሰ	"ፈረከሰ"

ተፈረካከሰ	"ፈረከሰ"
ተፈረደ	-"ፈረደ"
ተፈረፈረ	-"ፈረፈረ"
ተፈራ	-"ፈራ"
ተፈራረመ	-"ፈረመ"
ተፈራረቀ	-"*ፈረቀ"
ተፈራገጠ	-"*ፈረገጠ"
ተፈሰከ/ተፈሰገ/	"ፈሰከ"
ተፈቀረ	-"*ፈቀረ"
ተፈቀደ	-"ፈቀደ"
ተፈቃቀረ	-"*ፈቀረ"
ተፈቃቀደ	-"ፈቀደ"
ተፈተሰከ	"*ፈተሰከ"
ተፈተነ	-"ፈተነ"
ተፈታ	-"ፈታ"
ተፈታተነ	-"ፈተነ"
ተፈታተገ	"ፈተገ"
ተፈታታ	-"ፈታ"
ተፈታታኝ	-"ፈተነ"
ተፈታኝ	-"ፈተነ"
ተፈነቀለ	-"ፈነቀለ"
ተፈነቸረ	-"ፈነቸረ"
ተፈነደሰ	-"*ፈነደሰ^1"
ተፈነዳደሰ	-"*ፈነደሰ^2"
ተፈነገለ	-"ፈነገለ"
ተፈነጠረ	-"*ፈነጠረ"
ተፈነጣጠረ	-"*ፈነጠረ"
ተፈናቀለ	-"ፈነቀለ"
ተፈናቃይ	-"ፈነቀለ"
ተፈናጠቀ	-"ፈነጠቀ"
ተፈናጠረ	"*ፈነጠረ"
ተፈናጠጠ	"*ፈነጠጠ"
ተፈናጣጭ	"*ፈነጠጠ"
ተፈናፈነ	"*ፈነፈነ"
ተፈወሰ	"ፈወሰ"
ተፈገመ	-"ፈገመ"
ተፈገፈገ	-"ፈገፈገ"
ተፈጠመ	"*ፈጠመ"
ተፈጠረ	-"ፈጠረ^1"
ተፈጠረቀ	-"ፈጠረቀ"
ተፈጠፈጠ	-"ፈጠፈጠ"
ተፈጣጠመ	"*ፈጠመ"
ተፈጥሮ	"ፈጠረ^1"
ተፈፀመ	-"ፈፀመ"
ተፈፃሚ	-"ፈፀመ"
ተፋለመ	-"ፈለመ"
ተፋለሰ	"ፈለሰ"
ተፋላሚ	-"ፈለመ"
ተፋረሰ	-"ፈረሰ"
ተፋረደ	-"ፈረደ"
ተፋራጅ	"ፈረደ"

ተፋሰሰ	-"ፈሰሰ"
ተፋሰሰ	"ፈሰሰ"
ተፋተተ	-"ፈተተ"
ተፋተገ	-"ፈተገ"
ተፋታ	"ፈታ"
ተፋጀ^1	-"ፈጀ^1"
ተፋጀ^2	-"ፈጀ^2"
ተፋጠነ	-"ፈጠነ"
ተፋጠጠ	-"ፈጠጠ"
ተፋጨ	-"ፈጨ"
ተፋፈረ	-"አፈረ"
ተፋፈነ	-"አፈነ^1"
ተፋፋገ	-"አፈገ"
ተፋፋመ	-"ፋመ"
ተፍለከለከ	-"*ፈለከለከ"
ተፍለቀለቀ	-"ፈለቀ"
ተፍረመረመ	-"*ፈረመረመ"
ተፍረቀረቀ	"*ፈረቀረቀ"
ተፍረገረገ	"*ፈረገረገ"
ተፍረጠረጠ	-"ፈረጠ"
ተፍተለተለ	-"*ፈተለተለ"
ተፍታታ	-"ፈታ"
ተፍገመገመ	"*ፈገመገመ"
ተፍጨረጨረ	-"*ፈጨረጨረ"
ተፍጨርጨረ	-"*ፈጨረጨረ"
ተፎካከረ	-"ፎከረ"
ተፎካሪ	-"ፎከረ"
ተፎገረ	-"ፎገረ^2"

ቷ

ታመመ	-"አመመ^1"
ታመነ	"አመነ"
ታማ	-"አማ"
ታማሚ	-"አመመ^1"
ታማኝ	-"አመነ"
ታረመ	-"አረመ"
ታረሰች	-"አረሰ^2"
ታረቀ	-"*አረቀ"
ታረዘ	"*አረዘ"
ታሰበ	"አሰበ"
ታሸ	-"*አሸ"
ታቀበ	-"*አቀበ"
ታቀፈ	-"አቀፈ"
ታበለ	"አበለ"
ታተመ	-"አተመ"
ታተተ	-"አተተ"
ታነቀ	-"አነቀ"
ታነፀ	"አነፀ"
ታኘከ	-"አኘከ"

ታከመ	-"አከመ"
ታከረ	-"አከረ^1"
ታከከ	"አከከ"
ታካሚ	-"አከመ"
ታወረ	-"አወረ"
ታወቀ	-"አወቀ"
ታወከ	-"አወከ"
ታወደ	-"አወደ^2"
ታወጀ	"አወጀ"
ታዋቂ	-"አወቀ"
ታዘለ	-"አዘለ"
ታዘዘ	-"አዘዘ"
ታዛዥ	-"አዘዘ"
ታየ	-"አየ"
ታደለ	-"አደለ"
ታደመ	-"አደመ^2"
ታደሰ	-"አደሰ"
ታደነ	-"አደነ"
ታዳሚ	-"አደመ^2"
ታጀለ	-"አጀለ"
ታገተ	-"አገተ"
ታገዘ	"አገዘ"
ታጋሽ	-"ታገሰ"
ታጋች	-"አገተ"
ታገለ	-"አገለ"
ታጠበ	"አጠበ"
ታጠፈ	"አጠፈ"
ታጣ	-"አጣ"
ታጣፊ	"አጠፈ"
ታጨቀ	-"አጨቀ"
ታፈረ	-"አፈረ"
ታፈሰ	-"አፈሰ"
ታፈነ	-"አፈነ"
ታፈገ	"አፈገ"
ትንቅንቅ	-"አነቀ"

አለ

አለመለመ	-"ለመለመ^1"
አለመነ	"ለመነ"
አለመደ	"ለመደ"
አለመጠ	-"ለመጠ^1"
አለማመጠ	-"ለመጠ"
አለሰለሰ	-"ለሰለሰ"
አለሳለሰ	-"ለሰለሰ"
አለቀለቀ	-"ለቀለቀ"
አለቀመ	"ለቀመ"
አለቀሰ	-"*ለቀሰ"
አለቀቀ	-"ለቀቀ"
አለቀተ	-"ለቀተ"
አለቃለቀ	"ለቀለቀ"
አለቃቀሰ	-"*ለቀሰ"
አለቅላቂ	-"ለቀለቀ"
አለበሰ	-"ለበሰ"
አለባበሰ	-"ለበሰ"
አለተለተ	"ለተለተ"
አለከለከ	-"ለከለከ^1"
አለከፈ	-"ለከፈ"
አለካካ	-"ለካ^1"
አለኳኳሰ	-"ለኰሰ"
አለዋወጠ	-"ለወጠ"
አለዘበ	-"ለዘበ"
አለዘዘ	-"ለዘዘ"
አለያየ	-"ለየ"
አለደለደ	-"ለደለደ"
አለገገ	-"*ለገገ"
አለጎመ	"ለጎመ"
አለጠለጠ	-"ለጠለጠ"
አለጣጠቀ	-"ለጠቀ"
አለፋ	"ለፋ"
አለፋለፈ	-"ለፈለፈ"
አለፋጨቀ	-"ለፈጨቀ"
አላላ	-"ላላ"
አላመ	-"ላመ"
አላሞጠ	-"*ላመጠ"
አላሰ	-"ላሰ"
አላቀ	-"ላቀ"
አላቀሰ	"*ለቀሰ"
አላቀቀ	-"ለቀቀ"
አላቆጠ	-"ላቆጠ"
አላበ	"*ላበ"
አላባሸ	"ለበሰ"
አላተመ	-"ለተመ"
አላተነ	-"ላተነ"
አላከከ	-"ላከከ"
አላከፈ	"ለከፈ"
አላኮሰ	-"ለኮሰ"
አላኳሸ	-"ለኰሰ"
አላወሰ	-"*ላወሰ"
አላወጠ	-"ለወጠ"
አላገጠ	-"*ለገጠ"
አላጋ	-"ለጋ^1"
አላጋጭ	-"*ላገጠ"
አላጠቀ	-"ለጠቀ"
አልመዘመዘ	"*ለመዘመዘ"
አልሚ ምግብ	-"ለማ"
አልቃሻ	-"*ለቀሰ"
አልቃሽ	-"*ለቀሰ"
አልባሽ	-"ለበሰ"
አልከሰከሰ	-"* ለከሰከሰ"
አልከፈከፈ	"ለኮፈ"
አልኮሰኮሰ	-"ለኰሰ"

አልኮፈኮፈ	"ለኮፈ"
አልገዘገዘ	-"*ለገዘገዘ"
አልጎመጎመ	-"ለጎመ"
አልፈሰፈሰ	-"*ለፈሰፈሰ"
አልፉ	-"ለፋ"

አመ

አመሃኘ	-"*መከኘ"
አመለከ	-"*መለከ"
አመለከተ	-"*መለከተ"
አመለካከት	"*መለከተ"
አመሳሰሰ	" መሰሰ"
አመሳከተ	-"*መለከተ"
አመልካች	-"*መለከተ"
አመረረ	"መረረ"
አመረቀዘ	-"መረቀዘ"
አመረተ	-"መረተ"
አመረገደ	"መረገደ"
አመራ	-"መራ"
አመራመረ	-"መረመረ"
አመራር	"መራ"
አመሰቃቀለ	-"*መሰቀለ"
አመሰገነ	-"*መሰገነ"
አመሰጠረ	-"*መሰጠረ"
አመሳሰለ	-"መሰለ"
አመሳቀለ	-"*መሰቀለ"
አመሸ	"መሸ"
አመሸከ	-"መሸከ"
አመሻሸ	"መሸ"
አመቸ	"*መቸ"
አመቺ	"*መቸ"
አመቻቸ	-"*መቸ"
አመነሸ	-"መነሸ"
አመነኮሰ	-"መነኮሰ"
አመነጨ	-"መነጨ"
አመነቀረ	-"መነቀረ"
አመናጨቀ	-"*መነጨቀ"
አመካኘ	-"*መከኘ"
አመዘነ	-"መዘነ"
አመዛዘነ	-"መዘነ"
አመዛዛኝ	-"መዘነ"
አመገለ	-"መገለ"
አመጠቀ	-"መጠቀ"
አመጠጠ	-"መጠጠ"
አመፃደቀ	-"*መፀደቀ"
አሙለጨለጨ	-"ሟለጨ"
አማለደ	-"ማለደ^{2}"
አማላጅ	-"ማለደ^{2}"
አማረረ	-"መረረ"
አማረጠ	-"መረጠ"
አማራጭ	"መረጠ"
አማሰለ	-"መሰለ"
አማተረ	-"ማተረ"
አማታ	-"መታ^{1}"
አማከለ	"*ማከለ"
አማከረ	-"መከረ"
አማካሪ	"መከረ"
አማካይ	-"*ማከለ"
አማዘዘ	-"መዘዘ"
አማገ	-"ማገ"
አማገጠ	-"ማገጠ"
አማጠ	"*ማጠ"
አማጭ	"መጣ"
አማፀነ	-"*ማፀነ"
አምራች	-"መረተ^{1}"
አምባረቀ	-"ባረቀ"
አምባቀቀ	-"*በቀቀ"
አምታታ	"መታ^{1}"
አምታች	-"መታ^{1}"
አምቧተረ	"*ቧተረ"
አምነሸነሸ	"*መነሸነሸ"
አምዘገዘገ	"*መዘገዘገ"
አሞለሞለ	-"ሞለሞለ"
አሞላቀቀ	-"*ሞለቀቀ"
አሞላፈጠ	-"*ሞለፈጠ"
አሞቀሞቀ	-"ሞቀሞቀ"
አሞተ	-"ሞተ"
አሞናሞነ	-"*ሞነሞነ"
አሞናደለ	-"*ሞነደለ"
አሞኘ	-"*ሞኘ"
አሞካሸ	-"*ሞከሸ"
አሞዳሞደ	-"*ሞደሞደ"
አሞገሰ	-"*ሞገሰ"
አሞጣሞጠ	-"ሞጠሞጠ"
አሞጨሞጨ	-"ሞጨሞጨ"
አሟለጠ	-"ሟለጠ"
አሟለጨ	"ሟለጨ"
አሟላ	-"ሞላ^{1}"
አሟሟቀ	-"ሞቀ"
አሟሟቂ	-"ሞቀ"
አሟሟት	-"ሞተ"
አሟረተ	-"*ሟረተ"
አሟሸ	-"*ሟሸ"
አሟነነ	-"ሟነነ"
አሟገተ	-"ሞገተ"
አሟጠጠ	-"ሟጠጠ"
አሟጨ	-"ሟጨ"

አረ

አረመደ	-"*ረመደ"
አረማመደ	-"*ረመደ"
አረማመድ	"*ረመደ"
አረሰረሰ	-"ረሰረሰ"
አረሳሳ	-"ረሳ"
አረቀቀ	-"ረቀቀ"
አረበረበ	-"ረበረበ"
አረባ	-"ረባ"
አረብራቢ	"ረበረበ"
አረከሰ	-"ረከሰ"
አረካ	-"ረካ"
አረካከበ	-"*ረከበ^{2}"
አረካካቢ	"*ረከበ^{2}"
አረዘመ	-"ረዘመ"
አረገረገ	-"*ረገረገ"
አረገዘ	"*ረገዘ"
አረገደ	-"ረገደ"
አረጋ	"ረጋ"
አረጋገጠ	-"*ረገጠ"
አረጋጋ	"ረጋ"
አረግራጊ	"*ረገረገ"
አረጠበ	-"ረጠበ^{1}"
አረፈቀ	-"ረፈቀ"
አረፈደ	"ረፈደ"
አራመደ	"*ረመደ"
አራማጅ	-"*ረመደ"
አራራቀ	-"ራቀ"
አራስ	"ራስ"
አራቀ	-"ራቀ"
አራቀቀ	-"ረቀቀ"
አራቆተ	"*ራቆተ"
አራበሸ	-"ረበሸ"
አራከሰ	-"ረከሰ"
አራኮተ	-"*ረኮተ"
አራወጠ	-"*ረወጠ"
አራዘመ	-"ረዘመ"
አራደ	-"ራደ"
አራገበ	-"*ረገበ"
አራጋቢ	-"*ረገበ"
አራገፈ	"ረገፈ"
አራጠበ	-"ረጠበ^{1}"
አርመጠመጠ	-"ረመጠ"
አርቃቂ	"ረቀቀ"
አርበተበተ	-"*ረበተበተ"
አርበደበደ	-"*ረበደበደ"
አርከፈከፈ	-"*ረከፈከፈ"
አርኪ	-"ረካ"
አርገበገበ	-"*ረገበ"
አርገደገደ	-"ረገደ"
አርገፈገፈ	-"*ረገፈገፈ"
አርጋጅ	-"ረገደ"
አርጣጣ	"ረጠጠ"
አርፋጅ	-"ረፈደ"
አሮጠ	-"ሮጠ"
አሯሯጠ	-"ሮጠ"

አሰ

አሰለለ	-"ሰለለ"
አሰለመ	-"ሰለመ^{1}"
አሰለሰ	-"ሰለሰ"
አሰለሰለ	"ሰለሰለ"
አሰለቸ	-"ሰለቸ"
አሰለጠ	-"ሰለጠ"
አሰለጠነ	"ሰለጠነ"
አሰለፈ	-"ሰለፈ"
አሰላ^{1}	-"ሰላ^{3}"
አሰላ^{2}	"*ሰላ"
አሰላለፍ	-"ሰለፈ"
አሳላፊ	-"ሰለፈ"
አሰልቺ	-"ሰለቸ"
አሰልጣኝ	-"ሰለጠነ"
አሰመረ^{1}	-"ሰመረ"
አሰመረ^{2}	-"*ሰመረ"
አሰመጠ	-"ሰመጠ"
አሰማ	-"ሰማ^{2}"
አሰማ	-"ሰማ^{1}"
አሰማራ	-"*ሰማራ"
አሰረረ	-"ሰረረ"
አሰረፀ	-"ሰረፀ"
አሰሪ	-"ሰራ^{1}"
አሰራ	"ሰራ^{1}"
አሰራር	-"ሰራ^{1}"
አሰራጨ	-"*ሰረጨ"
አሰቃቂ	"ሰቀቀ^{1}"
አሰቃየ	-"*ሰቀየ"
አሰባ	-"ሰባ"
አሰባሰበ	-"ሰበሰበ"
አሰባቀለ	-"*ሰበቀለ"
አሰባጠረ	"ሰበጠረ/ሰባጠረ/"
አሰነበተ	-"ሰነበተ"
አሰነፈ	-"ሰነፈ"
አሰናበተ	-"ሰነበተ"
አሰናኘ	-"*ሰነኘ"
አሰናከለ	-"ሰነከለ"
አሰናዳ	-"*ሰነዳ"
አሰኘ	-"*ሰኘ"
አሰከረ	-"ሰከረ"
አሰየፈ	"ሰየፈ"

አሰደበ	-"ሰደበ"
አሰዳቢ	-"ሰደበ"
አሰገደ	-"ሰገደ"
አሰገገ	-"ሰገገ"
አሰጋ	-"ሰጋ"
አሰጠመ	-"ሰመጠ"
አሰጣ	-"*ሰጣ"
አሰፈረ	-"ሰፈረ^{2}"
አሰፈሰፈ	"*ሰፈሰፈ"
አሰፈነ	-"ሰፈነ"
አሰፈፈ	-"ሰፈፈ"
አሰፋ	-"ሰፋ^{2}"
አሰፉ	-"ሰፉ^{1}"
አሳለ	-"ሳለ^{3}"
አሳለመ	-"*ሰለመ"
አሳለፈ	"አለፈ"
አሳሳ	-"ሰሳ^{2}"
አሳሳፈ	-"አለፈ"
አሳመመ	-"አመመ^{1}"
አሳመነ	-"አመነ"
አሳመፀ	-"አመፀ"
አሰማ	-"ሰማ^{1}"
አሳማኝ	-"አመነ"
አሳረረ	-"አረረ"
አሳረሰ	-"አረሰ^{1}"
አሳረገ	"አረገ"
አሳረፈ	-"አረፈ"
አሳራሽ	-"አረሰ^{1}"
አሳራፊ	-"አረፈ"
አሳሰበ	-"አሰበ"
አሳሳ^{1}	-"ሳሳ^{1}"
አሳሳ^{2}	-"ሳሳ^{2}"
አሳሳቀ	-"ሳቀ"
አሳሳተ	-"ሳተ"
አሳሳች	-"ሳተ"
አሳሳቢ	-"አሰበ"
አሳቀ	-"ሳቀ"
አሳቀለ	-"ሰቀለ"
አሳቀቀ	"ሰቀቀ^{1}"
አሳቀፈ	-"አቀፈ"
አሳበረ	-"ሰበረ"
አሳበቀ	"ሰበቀ^{2}"
አሳበበ	-"*ሰበበ"
አሳበደ	-"አበደ"
አሳባቂ	"ሰበቀ^{2}"
አሳተ	"ሳተ"
አሳተመ	-"አተመ"
አሳተፈ	"*ሰተፈ"
አሳታሚ/ድርጅት/	-"አተመ"
አሳነፈ	"ሰነፈ"
አሳከመ	-"አከመ"

አሳከረ	-"ሰከረ"
አሳከከ	-"አከከ"
አሳወቀ	-"አወቀ"
አሳወደ	-"አወደ^{2}"
አሳወጀ	-"አወጀ"
አሳዘነ	-"አዘነ"
አሳየ	-"አየ"
አሳደመ	"አደመ^{1}"
አሳደረ	-"አደረ"
አሳደደ	-"ሰደደ"
አሳደገ	-"አደገ"
አሳዳሪ	-"አደረ"
አሳዳጅ	-"ሰደደ"
አሳዳጊ	-"አደገ"
አሳጠነ	"አጠነ"
አሳጣ	-"አጣ"
አሳፈረ	-"አፈረ"
አሳፈረ	-"ሰፈረ^{2}"
አሳፋሪ	-"አፈረ"
አሴረ	-"*ሰየረ"
አሰለመለመ	-"ሰለመ^{2}"
አስለመነ	-"ለመነ"
አስለመደ	"ለመደ"
አስለቀሰ	-"*ለቀሰ"
አስለቀቀ	-"ለቀቀ"
አስለቃሽ	"*ለቀሰ"
አስለከለከ	-"ለከለከ^{1}"
አስለወጠ	"ለወጠ"
አስለፈለፈ	-"ለፈለፈ"
አስለፋ	-"ለፋ"
አስመለመለ	-"መለመለ"
አስመለሰ	-"መለሰ"
አስመለከተ	-"*መለከተ"
አስመረረ	-"መረረ"
አስመረቀ	-"መረቀ"
አስመረቀነ	-"መረቀነ"
አስመረኮዘ	-"*መረኮዘ"
አስመረጠ	"መረጠ"
አስመራጭ	-"መረጠ"
አስመሰለ	-"መሰለ"
አስመሳይ	-"መሰለ"
አስመሰከረ	-"መሰከረ"
አስመሰገነ	-"*መሰገነ"
አስመሸ	-"መሸ"
አስመነመነ	-"*ሰመነመነ"
አስመካ	"*መካ"
አስመዘነ	-"መዘነ"
አስመዘገበ	-"መዘገበ"
አስመጣ	-"መጣ"
አስማማ	-"ሰማ^{1}"
አስማሚ	-"ሰማ^{1}"

አስማገጠ	-"*ማገጠ"
አስረቀረቀ	-"*ረቀረ$_2$ቀ"
አስረከበ	-"*ረከበ^{2}"
አስረዘመ	-"ረዘመ"
አስረዳ	-"*ረዳ"
አስረጀ^{1}	-"አረጀ"
አስረጀ^{2}	"*ረዳ"
አስረገዘ	"*ረገዘ"
አስረገደ	-"ረገደ"
አስረገጠ^{1}	-"ረገጠ"
አስረገጠ^{2}	-"*ረገጠ"
አስረጋጭ	-"ረገጠ"
አስሰለሰ	"ሰለሰ^{2}"
አስሾመ	-"ሾመ"
አስቀላመደ	"ቀላመደ"
አስቀመጠ	"*ቀመጠ"
አስቀማ	-"ቀማ"
አስቀረ	-"ቀረ"
አስቀሳፈተ	"ቀሳፈተ"
አስቀበረ	-"ቀበረ"
አስቀባዠረ	"ቀባዠረ"
አስቀባጠረ	"ቀባጠረ"
አስቀና	-"ቀና^{1}"
አስቀኘ	-"*ቀኘ"
አስቀየመ	-"*ቀየመ"
አስቀያሚ	-"*ቀየመ"
አስቀደመ	"ቀደመ"
አስቀደሰ	"ቀደሰ"
አስቀደደ	-"ቀደደ"
አስቀዳሽ	"ቀደሰ"
አስቀጠረ	-"ቀጠረ^{2}"
አስቀፀለ	-"ቀፀለ"
አስቂኝ	-"ሳቀ"
አስቆመ	-"ቆመ"
አስቆረበ	"ቆረበ"
አስቆረጠ	-"ቆረጠ"
አስቆራቢ	"ቆረበ"
አስቆጣ	-"*ቆጣ"
አስቆጨ	-"ቆጨ"
አስቋፈ	-"ቋፈ"
አስበለጠ	"በለጠ^{1}"
አስበላ	-"በላ"
አስበየነ	-"በየነ"
አስተሳለፈ	"አለፈ"
አስተማመነ	-"አመነ"
አስተማማኝ	-"አመነ"
አስተማረ	-"*መሃረ"
አስተማሪ	-"*መሃረ"
አስተረጎመ	-"ተረጎመ"
አስተርጓሚ	"ተረጎመ"
አስተሰረየ	-"*ሰረየ"

አስተሳሰበ	"አሰበ"
አስተሳሰብ	-"አሰበ"
አስተባበለ	-"አበለ"
አስተባበረ	-"አበረ"
አስተባባሪ	-"አበረ"
አስተቸ	-"ተቸ"
አስተነተነ	-"ተነተነ"
አስተነፈሰ	"ተነፈሰ"
አስተናባሪ	-"አስተናበረ"
አስተናገደ	-"*ነገደ"
አስተናጋጅ	-"*ነገደ"
አስተንታኝ	-"ተነተነ"
አስተኛ	"ተኛ"
አስተካከለ	-"አከለ^{1}"
አስተኮሰ	-"ተኮሰ"
አስተኳሽ	-"ተኮሰ"
አስተዋወቀ	-"አወቀ"
አስተዋዋቂ	-"አወቀ"
አስተዛዘለ	-"አዘለ"
አስተዛዘበ	"ታዘበ"
አስተዛዘነ	-"አዘነ"
አስተያየ	"አየ"
አስተዳደረ	"አደረ"
አስተዳዳሪ	-"አደረ"
አስተዳደር	-"አደረ"
አስተዳደግ	" አደገ"
አስተፋ	"ተፋ"
አስታመመ	-"አመመ^{1}"
አስታረቀ	"*አረቀ"
አስታራቂ	"*አረቀ"
አስታቀፈ	"አቀፈ"
አስታከከ	-"አከከ"
አስታወቀ	-"አወቀ"
አስታወከ	-"*አወከ"
አስታዋሽ	-"ታወሰ"
አስታገሰ	-"ታገሰ"
አስታጎለ	-"አጎለ"
አስታጠቀ	-"ታጠቀ"
አስቸኮለ	"ቸኮለ"
አስቸኳይ	-"ቸኮለ"
አስቸገረ	-"ቸገረ"
አስቸጋሪ	"ቸገረ"
አስቻለ	-"ቻለ"
አስነሰረ	-"ነሰረ"
አስነሳ	-"*ነሳ"
አስነበበ	-"*ነበበ"
አስነከሰ	-"እነከሰ"
አስነካ	-"ነካ"
አስነወረ	-"*ነወረ"
አስነዋሪ	-"*ነወረ"
አስነገረ	"ነገረ"

አስነኀተ	-"*ነኀተ"
አስነጠሰ	"*ነጠሰ"
አስናቀ	"ናቀ"
አስከበረ	-"ከበረ"
አስከተለ	-"*ከተለ"
አስከታይ	-"ከተለ"
አስከነዳ	"ከነዳ"
አስከፋ	-"ከፋ"
አስከፌ	-"ከፋ"
አስካሪ	-"ሰከረ"
አስካካ	-"*ካካ"
አስኮረፈ	-"*ኮረፈ"
አስኮበለለ	-"ኮበለለ"
አስኮናኝ	-"ኮነነ"
አስወረደ	-"ወረደ"
አስወራ	-"*ወራ"
አስወሰደ	-"ወሰደ"
አስወቀሰ	"ወቀሰ"
አስወነጀለ	-"ወነጀለ"
አስወደደ	-"ወደደ"
አስወጋ	-"ወጋ"
አስዋበ	"*ዋበ"
አስዋኘ	-"ዋኘ"
አስዘነጠ	-"ዘነጠ"
አስደመመ	-"*ደመመ"
አስደበተ	-"*ደበተ"
አስደሳች	-"*ደሰተ"
አስደበደበ	-"ደበደበ^{1}"
አስደነሰ	-"ደነሰ"
አስደነቀ	-"ደነቀ"
አስደናቂ	-"ደነቀ"
አስደገመ^{1}	"ደገመ^{1}"
አስደገመ^{2}	-"ደገመ^{2}"
አስደገደገ	"*ደገደገ"
አስደገፈ	-"ደገፈ"
አስደግዳጊ	-"*ደገደገ"
አስጀመረ	-"ጀመረ"
አስገመተ	-"ገመተ"
አስገመገመ	-"*ገመገመ"
አስገረመ	-"ገረመ^{2}"
አስገራሚ	-"ገረመ^{2}"
አስገሳ	-"*ገሳ"
አስገበረ	-"ገበረ"
አስገበገበ	-"*ሰገበገበ"
አስገነዘበ	-"*ገነዘበ"
አስገኘ	-"*ገነኘ"
አስገደለ	-"ገደለ"
አስገደመ	"ገደመ"
አስገደደ	-"ገደደ^{2}"
አስገደፈ	-"ገደፈ^{1}"
አስጊ	"*ሰጋ"
አስጌጠ	-"*ገየጠ"
አስጎመጀ	-"ጎመጀ"
አስጎበኘ	-"ጎበኘ"
አስጎበኚ	-"ጎበኘ"
አስጓጎጠ	-"ጓጎጠ"
አስጠለለ	-"*ጠለለ^{2}"
አስጠላ	-"ጠላ^{2}"
አስጠማ	-"ጠማ"
አስጠራ	-"ጠራ^{1}"
አስጠቃ^{1}	-"ጠቃ"
አስጠቃ^{2}	-"*ጠቃ"
አስጠቆረ	-"ጠቆረ"
አስጠበቀ	"ጠበቀ^{1}"
አስጠነቀቀ	-"ጠነቀቀ"
አስጠነቆለ	-"ጠነቆለ^{1}"
አስጠና	-"*ጠና"
አስጠየቀ	"ጠየቀ"
አስጠገነ	-"ጠገነ"
አስጠጋ	-"*ጠጋ"
አስጠጣ	-"ጠጣ"
አስጣለ	-"ጣለ"
አስጨረሰ	-"ጨረሰ"
አስጨበጠ	-"ጨበጠ"
አስጨነቀ	-"ጨነቀ"
አስጨነገፈ	"ጨነገፈ"
አስጨፈረ	-"ጨፈረ"
አስፎሀ	"ፎሀ"
አስፀየፈ	"*ፀየፈ"
አስፀያፊ	-"*ፀየፈ"
አስፈለገ	-"ፈለገ"
አስፈላጊ	-"ፈለገ"
አስፈረደ	-"ፈረደ"
አስፈሪ	-"ፈራ"
አስፈራራ	-"ፈራ"
አስፈሳ	"ፈሳ"
አስፈቀደ	-"ፈቀደ"
አስፈነጠረ	-"ፈነጠረ"
አስፈፀመ	"ፈፀመ"
አስፈፃሚ	-"ፈፀመ"
አስፋፋ	-"ሰፋ^{2}"
አስፎገረ	-"ፎገረ^{2}"
አሶመሶመ	-"*ሶመሶመ"
አሶከሶከ	-"*ሶከሶከ"

አሸ

አሸለበ	-"ሸለበ"
አሸለተ	"ሸለተ"
አሸመቀ	-"ሸመቀ"
አሸማቀቀ	-"ሸመቀቀ"

አሸረጠ	-“*ሸረጠ”
አሸራሸ	-“*ሸረሸ”
አሸሸ	-“ሸሸ”
አሸቀሸቀ	-“ሸቀሸቀ^{1}”
አሸበረ	-“ሸበረ”
አሸበረቀ	-“*ሸበረቀ”
አሸበረከ	-“*ሸበረከ”
አሸበሸበ^{1}	-“ሸበሸበ”
አሸበሸበ^{2}	“*ሸበሸበ”
አሸባረ	-“ሸበረ”
አሸብራቂ	-“*ሸበረቀ”
አሸብሻቢ	-“*ሸበሸበ”
አሸቶ	-“ሸተ”
አሸነፈ	“*ሸነፈ”
አሸናከፈ	-“ሸነከፈ”
አሸናገረ	-“*ሸነገረ”
አሸናፊ	-“*ሸነፈ”
አሸንቋጠ	-“ሸነቆጠ”
አሸከመ	-“*ሸከመ”
አሸከሸከ	-“ሸከሸከ”
አሸጋሸገ	-“*ሸገሸገ”
አሸጋገረ	-“*ሻገረ”
አሸጠ	-“ሸጠ”
አሸፈተ	-“ሸፈተ^{1}”
አሻለ	-“*ሻለ”
አሻማ	-“*ሻማ”
አሻሚ	-“*ሻማ”
አሻረ	“ሻረ”
አሻረ	-“ሻረ”
አሻረከ	-“*ሸረከ”
አሻሸ	-“ አሸ”
አሻሻለ	-“*ሻለ”
አሻሻጠ	-“ ሸጠ”
አሻሻጭ	-“ ሸጠ”
አሻቀለ	-“ ሻቀለ”
አሻተተ	-“ ሸተተ”
አሻከረ	-“ ሻከረ”
አሻኮተ	-“*ሸኮተ”
አሻወከ	-“ ሸወከ”
አሻገረ	-“*ሻገረ”
አሻገተ	-“ ሻገተ”
አሻጋሪ	-“*ሻገረ”
አሻጠረ	-“ ሻጠረ”
አሻፈደ	-“ ሻፈደ”
አሻለገ	-“ ሸለገ^{3}”
አሸሉክለክ	-“ ሾለከ”
አሸመደመደ	-“*ሸመደመደ”
አሸሞነሞነ	“*ሸሞነሞነ”
አሸሟጠጠ	-“*ሸሞጠጠ”
አሽቀነደረ	-“*ቀነደረ”
አሽቀነጠረ	-“*ቀነጠረ”
አሽቀዳደመ	-“ቀደመ”
አሽቆለቆለ	-“ቆለቆለ”
አሽቆጠቆጠ	-“*ሸቆጠቆጠ^{1}”
አሽቆጠቆጠ	-“*ሸቆጠቆጠ^{2}”
አሽበለበለ	-“*ሸበለበለ”
አሽከረከረ	-“*ሸከረከረ”
አሽከርካሪ	-“*ሸከረከረ”
አሽካካ	-“*ካካ” ስር
አሽኮመኮመ	-“*ሸኮሞኮመ”
አሽኮረመመ	-“*ሸኮረመመ”
አሽኮነተረ	-“*ሸኮነተረ”
አሾለ	-“ሾለ”
አሾለከ	“ሾለከ”
አሾረ	-“ሾረ”
አሾቀ	-“ሾቀ”
አሾክሿኪ	-“ሹክ”
አሾጠጠ	-“ሾጠጠ”
አሾፈ	-“*ሾፈ”
አሿፊ	-“*ሾፈ”

አቀ

አቀለመ^{1}	-“ቀለመ^{1}”
አቀለመ^{2}	“*ቀለመ”
አቀለመደ	-“ቀላመደ”
አቀላወጠ	-“ቀላወጠ”
አቀላጠፈ	-“ቀለጠፈ”
አቀመሰ	-“ቀመሰ”
አቀመቀመ	-“ቀመቀመ^{2}”
አቀማመሰ	-“ቀመሰ”
አቀማመጥ	-“*ቀመጠ”
አቀማቀመ	-“*ቀመቀመ”
አቀማጠለ	-“*ቀማጠለ”
አቀረረ	-“ቀረረ”
አቀረሸ	-“ቀረሸ”
አቀረበ	-“ቀረበ”
አቀረና	-“ቀረና”
አቀራመተ	-“*ቀረመተ”
አቀራረበ	-“ቀረበ”
አቐራረበ	-“ቀረበ”
አቀሰሰ	-“ቀሰሰ^{1}”
አቀበለ	-“*ቀበለ”
አቀበረ	-“ቀበረ”
አቀበጠ	-“ቀበጠ”
አቀባበለ	-“*ቀበለ”
አቀባበል	-“*ቀበለ”
አቀባበረ	-“ቀበረ”
አቀታተረ	-“*ቀተረ”

አቀነባበረ	-"*ቀነበረ"
አቀነጻ	-"ቀነጻ^{1}"
አቀና	-"ቀና^{2}"
አቀናበረ	"*ቀነበረ"
አቀናባሪ	-"*ቀነበረ"
አቀናነሰ	-"ቀነሰ"
አቀናጀ	-"*ቀነጀ"
አቀናጣ	-"ቀነጣ"
አቀንቃኝ	-"ቀነቀነ^{2}"
አቀያየመ	"*ቀየመ"
አቀያያሚ	-"*ቀየመ"
አቀያየጠ	-"ቀየጠ"
አቀዳደመ	-"ቀደመ"
አቀጣጠለ^{1}	-"ቀጠለ"
አቀጣጠለ^{2}	-"*ቃጠለ"
አቀጨመ	-"*ቀጨመ^{1}"
አቀፈፈ	-"ቀፈፈ^{2}"
አቁለጨለጨ	-"ቁለጨ"
አቁላላ	-"ቁላ^{1}"
አቁራቢ	-"ቆረበ"
አቁስል	-"ቆሰለ"
አቁነጠነጠ	-"*ቆነጠነጠ"
አቃለለ	-"ቀለለ"
አቃለደ	-"ቀለደ"
አቃለጠ	-"ቀለጠ"
አቃልጣ	-"ቀለጠ"
አቃመ	-"ቃመ"
አቃመሰ	-"ቀመሰ"
አቃማ	-"ቀማ"
አቃረ	-"*ቃረ"
አቃረጠ	-"ቀረጠ"
አቃበረ	-"ቀበረ"
አቃቃ	-"ቃቃ"
አቃቃረ	-"*ቃቃረ"
አቃተተ	-"ቃተተ"
አቃና	"ቀና^{2}"
አቃወሰ	-"ቀወሰ"
አቃዠ	-"ቃዠ"
አቃጠለ	-"*ቃጠለ"
አቃጠረ	-"ቀጠረ^{2}"
አቃጣሪ	-"ቀጠረ^{2}"
አቃጨለ	-"ቃጨለ"
አቄለ	-"ቄለ"
አቄመ	-"*ቀየመ"
አቅለሰለሰ	-"ቀለሰ"
አቅለሸለሸ	-"*ቀለሸለሸ"
አቅለበለበ	-"*ቀለበለበ"
አቅለጠለጠ	-"ቀለጠ"
አቅለጥልጥ	-"ቀለጠ"
አቅልጥ	ቀለጠ"
አቅመደመደ	-"*ቀመደመደ"
አቅራሪ	-"*ቀረረ"
አቅራሩ	-"*ቀረረ"
አቅራቢ	-"ቀረበ"
አቅበጠበጠ	-"ቀበጠ"
አቅነዘነዘ	-"*ቀነዘነዘ"
አቅኚ	-"ቀና^{2}"
አቅዘመዘመ	-"*ቀዘመዘመ"
አቅበዘበዘ	-"ቃበዘ"
አቅጨለጨለ	-"ቃጨለ"
አቆለቆለ	-"ቆለቆለ"
አቆላመመ	-"ቆለመመ"
አቆላመጠ	-"*ቆለመጠ"
አቆላማጭ	-"*ቆለመጠ "
አቆልቋይ	-"ቆለቆለ"
አቆመ	-"ቆመ"
አቆረማመደ	-"*ቆረመደ"
አቆረበ	-"ቆረበ"
አቆረጠ	-"ቆረጠ"
አቆራመደ	-"*ቆረመደ"
አቆራረጠ	-"ቆረጠ"
አቆራፈደ	-"ቆረፈደ"
አቆራቆሰ	-"ቆረቆሰ^{1}"
አቆራቋሽ	- "ቆረቆሰ^{1}"
አቆራኘ	-"*ቆረኘ"
አቆርቋዥ	-"ቆረቆዘ^{1}"
አቆበቆበ	-"*ቆበቆበ"
አቆብቋቢ	"*ቆበቆበ"
አቆታች	-"*ቆተች"
አቆነጀ	-"ቆነጀ"
አቆናጠጠ	-"ቆነጠጠ"
አቆጋ	-"ቆጋ"
አቆጠቆጠ	-"ቆጠቆጠ^{2}"
አቆጣጠር	"ቆጠረ"
አቋመጠ	-"ቋመጠ"
አቋረሰ	-"ቆረሰ
አቋረጠ	-"ቆረጠ"
አቋራጭ	-"ቆረጠ"
አቋቋመ	-"ቆመ"
አቋቋም	-"ቆመ"
አቋተ	-"ቋተ"
አቋደሰ	-"*ቆደሰ"
አቋፈ	-"*ቋፈ^{2}"

አበ

አበለጠ	"በለሕ^{1}"
አበለፀገ	-"በለፀገ"
አበላ	-"በላ"
አበላሸ	-"*በለሸ"
አበላለጠ	-"በለጠ^{1}"

አበላሸ	-"*በለሸ"
አበረረ	-"በረረ"
አበረቀ	"በረቀ"
አበረታታ	-"በረታ"
አበረከተ	-"በረከተ"
አበረዘ	-"በረዘ"
አበረደ	-"በረደ"
አበራ	-"በራ^{1}"
አበራየ	-"*በረየ"
አበሰረ	-"*በሰረ"
አበሰበሰ	"በሰበሰ"
አበሳበሰ	-"በሰበሰ"
አበሳጨ	-"*በሰጨ"
አበሻቀጠ	-"በሸቀጠ"
አበቀለ	-"በቀለ"
አበቃ	-"በቃ"
አበነነ	-"በነነ"
አበከረ	"*በከረ"
አበዛ	-"በዛ"
አበደረ	-"*በደረ"
አበዳሪ	-"*በደረ"
አበጀ	-"በጀ^{2}"
አበጃጀ	-"በጀ^{2}"
አበገነ	-"በገነ"
አበጠረ^{1}	-"*በጠረ^{1}"
አበጠረ^{2}	-"*በጠረ^{2}"
አበጣበጠ	-"በጠበጠ"
አባለጠ	"በለጠ^{1}"
አባሳ	-"በሳ"
አባረረ	-"በረረ"
አባረቀ	-"ባረቀ"
አባረዘ	"በረዘ"
አባራ	-"በራ^{2}"
አባራሪ	-"በረረ"
አባቃ	"በቃ"
አባሰ	-"ባሰ"
አባበለ	-"*ባበለ"
አባባሰ	-"ባሰ"
አባካኝ	-"ባከነ"
አባዘተ	-"ባዘተ"
አብለጠለጠ	-"በለጠ^{2}"
አብለጨለጨ	"*በለጨ"
አብሳሳ	"በሳ"
አብራሪ	-"በረረ"
አብረቀረቀ	-"በረቀ"
አብረከረከ	-"በረከ"
አብረጀረጀ	-"*በረጀረጀ"
አብራራ	-"በራ^{1}"
አብራጅ	-"በረደ"
አብሳሪ	-"*በሰረ"
አብሰከሰከ	"በሰከ"
አብሶ	-"ባሰ"
አብሻቂ	-"በሸቀ^{2}"
አብሻቅ	-"በሸቀ^{2}"
አብቃቃ	-"በቃ"
አብከነከነ	-"ባከነ"
አብጋኝ	-"በገነ"
አብግን	-"በገነ"
አብጠለጠለ	-"*በጠለጠለ"
አብጠሰጠሰ	"በጠሰ"
አቦነነ	-"ቦነነ"
አቦዘነ	-"ቦዘነ"
አቧለተ	-"*ቧለተ"
አቧደነ	-"*ቧደነ"
አቧገተ	-"ቧገተ"

አተ

አተለቀ	-"ተለቀ"
አተረማመሰ	-"*ተራመሰ"
አተረተረ	"*ተረተረ"
አተረፈ	-"ተረፈ"
አተራመሰ	-"*ተራመሰ"
አተበተ	-"ተበተ"
አተባ	-"ተባ"
አተነነ	-"ተነነ"
አተኮረ	-"ተኮረ"
አተጋ	-"ተጋ"
አተፈተፈ	-"*ተፈተፈ"
አተፍታፊ	-"*ተፈተፈ"
አታለለ	-"*ታለለ"
አታላይ	-"*ታለለ"
አታረፈ	-"ተረፈ"
አታከተ	-"ታከተ"
አታካች	"ታከተ"
አታገለ	-"ታገለ"
አትረፈረፈ	-"ተረፈ"
አትራፊ	-"ተረፈ"
አትከነከነ	-"ተከነ"
አቶሰቶሰ	-"*ቶሰቶሰ"
አቶሰቷሽ	-"*ቶሰቶሰ"

አቸ

አቸከ	-"ቸከ"
አቻቻለ	-"ቻለ"
አቻኮለ	-"ቸኮለ"

አነ

አነረነረ	-"*ነረነረ"
አነሰረ	"ነሰረ"
አነሷ	-"*ነሳ"
አነሳሳ	-"*ነሷ"
አነሳሸ	-"*ነሳ"
አነቀረ	-"*ነቀረ"
አነቀሸ	-"*ነቀሸ"
አነቀፈ	-"ነቀፈ^2"
አነቃ	-"ነቃ^1"
አነቃቃ	-"ነቃ^1"
አነቃነቀ	-"ነቀነቀ"
አነቆረ	-"*ነቆረ"
አነቆጠ	"ነቆጠ"
አነበበ	-"*ነበበ"
አነበነበ	-"*ነበነበ"
አነባበረ	-"*ነበረረ"
አነባበረ	-"*ነበረበረ"
አነብናቢ	-"*ነበነበ"
አነቦጨ	-"ነቦጨ"
አነታረከ	-"ነተረከ"
አነኩተ	-"ነከተ"
አነካነከ	-"*ነከነከ"
አነካካ	-"ነካ"
አነኮረ	"ነኮረ"
አነወረ	-"*ነወረ"
አነዘረ	-"ነዘረ"
አነዘዘ	-"*ነዘዘ"
አነዛነዘ	-"ነዘነዘ"
አነዛናዥ	-"ነዘነዘ"
አነገሰ	-"ነገሰ"
አነገነገ	-"ነገነገ^2"
አነጋ	-"ነጋ"
አነጋገረ	"ነገረ"
አነጋገሰ	-"ነገሰ"
አነጋጋሪ	"ነገረ"
አነጎለ	"ነጎለ"
አነጎረ	-"ነጎረ"
አነጎተ	"*ነጎተ"
አነጎደ^1	-"ነጎደ^1"
አነጎደ^2	-"ነጎደ^2"
አነጠሰ	-"*ነጠሰ"
አነጠፈ	-"*ነጠፈ"
አነጣጠለ	-"ነጠለ"
አነጣጠረ	"*ነጠረ"
አነጣጣሪ	"*ነጠረ"
አነጫነጨ	-"*ነጨነጨ"
አነፃፀረ	-"*ነፀረ"
አነፈሰ	-"ነፈሰ"
አነፈነፈ	-"*ነፈነፈ^2"
አነፋለለ	-"ነፈለለ"
አነፋረቀ	-"ነፈረቀ"
አነፍናፊ	-"*ነፈነፈ^2"
አናቆረ	"*ነቆረ"
አናበበ	-"*ነበበ"
አናባቢ	-"*ነበበ"
አናናቀ	-"ናቀ"
አናከሰ	-"ነከሰ"
አናካ	-"ነካ"
አናወዘ	"ናወዘ"
አናወጠ	-"*ነወጠ"
አናዘዘ	-"ናዘዘ"
አናደደ	-"ነደደ^2"
አናዳጅ	-"ነደደ^2"
አናገረ	-"ነገረ"
አናጋ	-"*ነጋ"
አናጋሪ	-"ነገረ"
አናጠቀ	-"ነጠቀ"
አናጨ	-"ነጨ"
አናፈሰ	-"ነፈሰ"
አናፈጠ	-"*ነፈጠ"
አናፋሽ	-"ነፈሰ"

አን

አንሰለጀጀ	-"ሰለጀጀ"
አንሰረሰረ	-"*ሰረሰረ"
አንሰራፋ	-"*ሰረፋ"
አንሰፈሰፈ	-"*ሰፈሰፈ"
አንሳፈፈ	-"ሰፈፈ"
አንሸረሸረ	"*ሸረሸረ"
አንሸራሸረ	-"*ሸረሸረ"
አንሸራተተ	-"*ሸረተተ"
አንሸራታች	-"*ሸረተተ"
አንሸቀሸቀ	-"ሸቀሸቀ^2"
አንሸዋረረ	"*ሸወረረ"
አንሻረረ	-"*ሸረረ"
አንሻተተ	-"*ሸተተ"
አንሻፈፈ	-"ሸፈፈ"
አንሺ	-"*ነሳ"
አንሾካሾከ	-"ሹክ"
አንሿከከ	-"*ሾከከ"
አናጨ	"ነጨ"
አንቀለቀለ	-"*ቀለቀለ"
አንቀላበሰ	-"*ቀለበሰ"
አንቀረቀበ	-"*ቀረቀበ"
አንቀረበበ	-"*ቀረበበ"
አንቀረደደ	"ቀረደደ"

አንቀረፈፈ	-"*ቀረፈፈ"
አንቀራጨ	-"*ቀረጨ"
አንቀራፈፈ	-"*ቀረፈፈ"
አንቀሳቀሰ	-"*ቀሰቀሰ"
አንቀሽረረ	"ቀሸረረ"
አንቀሻቀሸ	-"*ቀሸቀሸ"
አንቀበቀበ	-"*ቀበቀበ"
አንቀበደደ	-"ቀበደደ"
አንቀባረረ	-"*ቀበረረ"
አንቀወቀወ	-"*ቀወቀወ"
አንቀዋለለ	-"*ቀወለለ"
አንቀዠቀዠ	-"*ቀዠቀዠ"
አንቀጠቀጠ	-"*ቀጠቀጠ"
አንቀጫቀጨ	-"*ቀጨቀጨ"
አንቀፈረረ	-"*ቀፈረረ"
አንቀፈደደ	-"*ቀፈደደ"
አንቂ	-"ንቃ"
አንቃረረ^{1}	-"ቀረረ"
አንቃረረ^{2}	-"*ቀረረ"
አንቃራሪ	-"ቀረረ"
አንቃቃ	-"ቃ"
አንቆረሰሰ	-"*ቆረሰሰ"
አንቆረቆረ	-"*ቆረቆረ"
አንቆረበበ	-"*ቆረበበ"
አንቆረዘዘ	-"*ቆረዘዘ"
አንቆረፈፈ	-"*ቆረፈፈ"
አንቆራባ	"ቆረባ"
አንቆራጠጠ	-"*ቆረጠጠ"
አንቆሻቆሸ	-"*ቆሸቆሸ"
አንቆሻበለ	-"*ቆሸበለ"
አንቆጠቆጠ	-"*ቆጠቆጠ^{2}"
አንቆጣቆጠ	-"*ቆጠቆጠ^{1}"
አንቆጨቆጨ	-"*ቆጨቆጨ"
አንቋሸሸ	-"ቆሸሸ"
አንቋቋ	-"ቋቋ"
አንበለበለ	-"*በለበለ"
አንበላጠጠ	-"በለጠጠ"
አንበረከከ	-"*በረከከ"
አንበራጠጠ	-"*በረጠጠ"
አንበሸበሸ	-"*በሸበሸ"
አንበከበከ	-"*በከበከ"
አንበዛበዘ	"*በዘበዘ"
አንበደበደ	"*በደበደ"
አንበጣረረ	-"*በጠረረ"
አንበጨበጨ	-"*በጨበጨ"
አንበጫበጨ	-"*በጨበጨ"
አንባረቀ	-"ባረቀ"
አንባቀቀ	-"*በቀቀ"
አንባቢ	-"*ነበበ"
አንቦለቦለ	-"*ቦለበለ"
አንቦረቀቀ	-"*ቦረቀቀ"
አንቦቀቦቀ	-"*ቦቀቦቀ"
አንቦዠቦዠ	"*ቦዠቦዠ"
አንቦገቦገ	-"*ቦገቦገ"
አንቦጫረቀ	"*ቦጨረቀ"
አንቦጫቦጨ	-"*ቦጨቦጨ"
አንቧቧ	-"*ቧቧ"
አንቧተረ	-"*ቧተረ"
አንቧታሪ	-"*ቧተረ"
አንቧቸ	-"*ቧቸ"
አንቧቸረ	-"*ቧቸረ"
አንተረከከ	-"ተረከከ"
አንተረፈፈ	-"*ተረፈፈ"
አንተራሰ	-"*ተረሰ"
አንተሰተሰ	-"*ተሰተሰ"
አንተበተበ	-"*ተበተበ^{2}"
አንተበተበ	-"*ተበተበ^{1}"
አንተከተከ	-"*ተከተከ"
አንተገተገ	-"ተገተገ^{1}"
አንታታ	"ታታ^{2}"
አንቷታ	- "ቷ^{2}"
አንቸረፈፈ	-"*ቸረፈፈ"
አንቸከቸከ	-"*ቸከቸከ"
አንቸፈረረ	-"*ቸፈረረ"
አንቻቻ	-"*ቻቻ"
አንከላወሰ	-"*ከለወሰ"
አንከረባበተ	-"ከረበተ"
አንከረተተ	-"*ከረተተ"
አንከረፈፈ	-"*ከረፈፈ"
አንከራተተ	"*ከረተተ"
አንከበከበ	-"*ከበከበ^{2}"
አንከባለለ	-"*ከበለለ"
አንከባከበ	-"*ከበከበ^{1}"
አንከተከተ	-"ከተከተ"
አንከወከወ	-"*ከወከወ"
አንከዋተተ	-"*ከወተተ"
አንካካ	-"*ካካ"
አንኮራፋ	-"*ኮረፈ^{2}"
አንኮሻኮሸ	-"ኮሸ"
አንኮፈኮፈ	-"*ኮፈኮፈ"
አንኳሰሰ	-"ኮሰሰ"
አንኳተተ	-"*ኮተተ"
አንዘለዘለ	-"ዘለዘለ"
አንዘላዘለ	-"ዘለዘለ"
አንዘረበበ	-"*ዘረበበ"
አንዘረዘረ	-"*ዘረዘረ"
አንዘረፈፈ	-"*ዘረፈፈ"
አንዘረጋ	-"ዘረጋ"
አንዘራጠጠ	-"ዘረጠጠ"
አንዘራፈጠ	-"*ዘረፈጠ"

አንዘፈዘፈ	-"*ዘፈዘፈ"
አንዘፈጠጠ	-"*ዘፈጠጠ"
አንዛረጠ	-"*ዘረጠ"
አንዛራጭ	-"*ዘረጠ"
አንዛዛ	-"*ዛዛ"
አንዠረገገ	-"ዠረገገ"
አንዠቀዠቀ	-"*ዠቀዠቀ"
አንዠባረረ	-"*ዠበረረ"
አንዠዋለለ	-"*ዠወለለ"
አንደላቀቀ	-"*ደለቀቀ"
አንደረበበ	-"*ደረበበ"
አንደረከከ	"*ደረከከ"
አንደረደረ	-"*ደረደረ"
አንደቀደቀ	-"*ደቀደቀ"
አንደበሰሰ	-"*ደበሰሰ"
አንደበዘዘ	-"*ደበዘዘ"
አንደበደበ	-"*ደበደበ"
አንደባለለ	-"ደበለለ^1"
አንደከደከ	-"*ደከደከ"
አንደፋደፈ	-"*ደፈደፈ"
አንደከከ	"ደከከ"
አንዱሰሰ	-"*ዱሰሰ"
አንዶለዶለ	-"*ዶለዶለ"
አንዶሸዶሸ	-"*ዶሸዶሸ"
አንጀለጀለ	-"*ጀለጀለ"
አንጀላጀለ	"*ጀለጀለ"
አንገለጀጀ	-"*ገለጀጀ"
አንገለጠጠ	-"ገለጠጠ"
አንገላታ	-"*ገለታ"
አንገላወደ	-"*ገላወደ"
አንገላጀጀ	-"*ገለጀጀ"
አንገረበበ	-"*ገረበበ"
አንገረዘበ	-"*ገረዘበ"
አንገሸገሸ	-"*ገሸገሸ"
አንገበገበ	-"*ገበገበ"
አንገብጋቢ	-"*ገበገበ"
አንገቸገቸ	-"*ገቸገቸ"
አንገዋለለ	-"*ገወለለ"
አንገዛገዘ	-"*ገዘገዘ"
አንገደገደ	-"*ገደገደ"
አንገጫገጨ	-"*ገጨገጨ"
አንገፈገፈ	-"*ገፈገፈ"
አንገፈጠጠ	-"*ገፈጠጠ"
አንጋለለ	-"*ጋለለ"
አንጋሸ	-"ነገሰ"
አንጋተተ	-"ገተተ"
አንጋጠጠ	-"*ገጠጠ"
አንጋደደ	-" ገደደ^1"
አንጓራደደ	-"*ጓረደደ"
አንጓደጓደ	-"*ጓደጓደ"

አንጓዳጓደ	-"ጉድ"
አንኳበበ	-"ኳበበ"
አንጠራራ	-"*ጠራራ"
አንጠራወዘ	-"*ጠራወዘ"
አንጠበጠበ	-"*ነጠበ"
አንጠባረረ	-"*ጠበረረ"
አንጠባጠበ^1	-"ጠብ"
አንጠባጠበ^2	-"ነጠበ"
አንጠፈጠፈ	-"*ጠፈጠፈ"
አንጣረሰ	-"ጠረሰ"
አንጣሪ	-" ነጠረ^1"
አንጣፊ	-"ነጠፈ"
አንጦለጦለ	-"*ጦለጦለ"
አንጦሸጦሸ	-"*ጦሸ"
አንጨረገገ	-"*ጨረገገ"
አንጨረፈፈ	-"*ጨረፈፈ"
አንጨፈረረ	-"*ጨፈረረ"
አንጫለጠ	-"ጨለጠ"
አንጫጫ	-"*ጫጫ"
አንፀባረቀ	-"*ፀበረቀ"
አንፀባራቂ	-"*ፀበረቀ"
አንፈረዘዘ	-"ፈረዘዘ"
አንፈራገጠ	-"*ፈረገጠ"
አንፈረፈረ	-"*ፈረፈረ"
አንፈጨፈጨ	-"*ፈጨፈጨ"
አንፎለፎለ	-"*ፎለፎለ"
አንፎደፎደ	-"ፎደፎደ"
አንፏቀቀ^1	-"*ፎቀቀ^1"
አንፏቀቀ^2	-"*ፎቀቀ^2"
አንፏቃቂ	-"*ፎቀቀ^2"
አናረ	-"ኖረ"
አናቀናቀ	-"*ኖቀኖቀ"
አናቃናቂ	-"*ኖቀኖቀ"
አናናረ	-"ኖረ"

አከ

አከማቸ	-"*ከመቸ"
አከራካሪ	-"*ከረከረ"
አከራየ	-"*ከረየ"
አከራይ	-"*ከረየ"
አከሰከሰ	-"ከሰከሰ"
አከሳከሰ	-"ከሰከሰ"
አከበበ	-"ከበበ"
አከታተለ	-"*ከተለ"
አከታከተ	-"ከተከተ"
አከነፈሰ	-"*ከነፈሰ"
አከናወነ	-"*ከነወነ"
አከንፋሽ	-"*ከነፈሰ"

አከፋ	-"ከፋ"
አከፋፈለ	-"ከፈለ"
አከፋፋ	"ከፋ"
አከፋፋይ	-" ከፈለ"
አኩራራ	-"ኮራ^{1}"
አኩራፋ	"*ኮረፈ^{1}"
አካለለ	-"ከለለ"
አካለበ	-"*ከለበ"
አካሰሰ	-"ከሰሰ"
አካካሰ	-"ካሰ"
አካፋይ	"ከፈለ"
አከለበለበ	-"ከለበ"
አከለፈለፈ	-"*ከለፈ"
አከራረ	"ከረረ"
አከሳሪ	-"ከሰረ"
አከሳይ	-"ከሰለ"
አከበሰበሰ	-"*ከበሰበሰ"
አከተፈተፈ	"*ከተፈ"
አከነፈነፈ	-"ከነፈ"
አከፋፋ	-"ከፋ"
አኮላተፈ	-"*ኮለተፈ"
አኮለታተፈ	-"*ኮለተፈ"
አኮለሸ	"*ኮለሸ"
አኮራ	-"ኮራ^{1}"
አኮራረፈ	-"*ኮረፈ^{1}"
አኮሳተረ	-"ኮሰተረ^{2}"
አኮበለለ	-"ኮበለለ"
አኮተኮተ	-"*ኮተኮተ"
አትኮትኳች	-"*ኮተኮተ"
አኮናተረ	-"*ኮናተረ"
አኮናታረ	-"*ኮናተረ"

አወ

አወለቀ	-"ወለቀ"
አወላለቀ	-"ወለቀ"
አወለካከፈ	-"ወለከፈ"
አወለወለ	-"ወለወለ"
አወለጋገደ	-"ወለገደ"
አወላመመ	-"*ወለመመ"
አወላከፈ	-"ወለከፈ"
አወላወለ	-"ወላወለ"
አወላዋይ	-"ወላወለ"
አወላዳ	-"*ወለዳ"
አወላገመ	-"ወለገመ"
አወላገደ	-"ወለገደ"
አወረሰ	-"ወረሰ"
አወረዛ	"ወረዛ"
አወረደ	-"ወረደ"
አወራ^{1}	-"*ወራ"
አወራ^{2}	-"*ወራ"
አወራረሰ	-"ወረሰ"
አወራረደ	-"ወረደ"
አወራጨ	-"*ወረጨ"
አወሰለተ	-"ወሰለተ"
አወሳ	-"*ወሳ"
አወሳሰበ	-"*ወሰበሰበ"
አወሳወሰ	-"ወሰወሰ"
አወሸናገረ	-"*ሸነገረ"
አወሻከተ	-"ወሸከተ"
አወሻገረ	-"ወሸገረ"
አወናበደ	-"ወነበደ"
አወናባጅ	-"ወነበደ"
አወናከረ	-"*ወነከረ"
አወናወነ	-"*ወነወነ"
አወነጨፈ	"ወነጨፈ"
አወናፈለ	-"*ወነፈለ"
አወካ	-"*ወካ"
አወዛ	-"ወዛ"
አወዛወዘ	-"ወዘወዘ"
አወዛገበ	"*ወዛገበ"
አወዛጋቢ	"*ወዛገበ"
አወያየ	"*ዋየ"
አወያይ	-"*ዋየ"
አወደለ	-"ወደለ^{1}"
አወደመ	-"ወደመ"
አወደሰ	-"*ወደሰ"
አወዳደረ	-"*ወደረ"
አወገዘ	-"*ወገዘ"
አወጋ	-"ወጋ"
አወጣ	-"ወጣ"
አወፈረ	-"ወፈረ"
አዋሃደ	-"*ወሃደ"
አዋለ	-"ዋለ^{1}"
አዋሰለ	-"ዋሰለ"
አዋለደ	-"ወለደ"
አዋለገ	-"ዋለገ"
አዋላጅ	-"ወለደ"
አዋረደ	-"ወረደ"
አዋራ	-"*ወራ"
አዋራጅ	-"ወረደ"
አዋሰ	-"*ዋሰ^{2}"
አዋሰነ	-"ወሰነ"
አዋሳኝ	-" ወሰነ"
አዋሸከ	"*ወሸከ"
አዋሻኪ	-"*ወሸከ"
አዋቀረ	-"ወቀረ"
አዋተተ	-"ዋተተ"
አዋከበ	-"*ወከበ"
አዋዋ	-"ዋዋ"
አዋዋለ	-"ዋለ^{2}"
አዋዛ	-"*ዋዛ"

ኣዋየ	-"*ዋየ"
ኣዋይ	-"ዋለ^{1}"
ኣዋደደ	-"ወደደ"
ኣዋጊ	-"ወጋ"
ኣዋጋ	-"ወጋ"
ኣዋጠ	-"ዋጠ"
ኣዋጣ	-"ወጣ"
ኣውለቀለቀ	-"ወለቀ"
ኣውለበለበ	-"*ወለበ"
ኣውራጅ	-"ወረደ"
ኣውሸለሸለ	-"ወሸለ"
ኣውተረተረ	-"*ወተረ"
ኣውተበተበ	-"ወተበተበ"
ኣውተፈተፈ	-"ወተፈ"
ኣውካካ	-"*ወካ"
ኣውጠንጠን	-"ወጠን"
ኣውጣጣ	-"ወጣ"

ኣዘ

ኣዘለቀ	-"ዘለቀ"
ኣዘመመ	-"ዘመመ^{1}"
ኣዘመረ	-"ዘመረ"
ኣዘመተ	"ዘመተ"
ኣዘረዘረ	-"ዘረዘረ"
ኣዘረጠ	-"*ዘረጠ"
ኣዘራ	-"ዘራ"
ኣዘቀዘቀ	-"ዘቀዘቀ"
ኣዘቀጠ	-"ዘቀጠ"
ኣዘበራረቀ	"ዘባረቀ"
ኣዘበጠ	-"ዘበጠ"
ኣዘባረቀ	-"ዘባረቀ"
ኣዘባንን	-"ዘበነን"
ኣዘነበ	-"ዘነበ"
ኣዘንበለ	-"*ዘንበለ"
ኣዘንጋጋ	-"ዘንጋ"
ኣዘነጠ	-"ዘነጠ"
ኣዘናዘነ	-"ዘነዘነ"
ኣዘናጊ	-"ዘነጋ"
ኣዘናጋ	-"ዘነጋ"
ኣዘከረ	-"ዘከረ"
ኣዘውተረ	-"*ዘወተረ"
ኣዘውታሪ	-"*ዘወተረ"
ኣዘዋወረ	-"ዞረ"
ኣዘገመ	-"*ዘገመ"
ኣዘገየ	-"ዘገየ"
ኣዘገጠ	-"ዘገጠ"
ኣዘጊ	-"*ዘጋ"
ኣዘጋ	-"ዘጋ"
ኣዘጋጀ	."*ዘገጀ"
ኣዘጋጅ	-"*ዘገጀ"
ኣዘጠዘጠ	-"*ዘጠዘጠ"
ኣዘጥዛጭ	-"*ዘጠዘጠ"
ኣዛለ	-"ዛለ"
ኣዛለቀ	-"ዘለቀ"
ኣዛመተ	-"ዘመተ"
ኣዛመደ	-"*ዘመደ"
ኣዛማጅ	-"*ዘመደ"
ኣዘረፈ	-"*ዘረፈ"
ኣዛባ	-"ዘባ"
ኣዛነቀ	"ዘነቀ"
ኣዛቆነ^{1}	-"ዛቆነ^{1}"
ኣዛቆነ^{2}	-"ዘቆነ^{2}"
ኣዛበረ	-"ዛበረ"
ኣዛነፈ	-"*ዘነፈ"
ኣዛወረ	-"ዞረ"
ኣዛገ	-"ዛገ"
ኣዜመ	"*ዘየመ"
ኣዝለገለገ	-"*ዘለገለገ"
ኣዝለፈለፈ	-"*ዘለፈለፈ"
ኣዝማሪ	-"ዘመረ"
ኣዝማች	-"ዘመተ"
ኣዝረበረበ	-"*ዘረበረበ"
ኣዝረከረከ	-"*ዘረከረከ"
ኣዝረጠረጠ	-"*ዘረጠ"
ኣዝረፈረፈ	-"*ዘረፈ"
ኣዝቦጠቦጠ	-"*ዘቦጠቦጠ"
ኣዝናና	-"ዘና"
ኣዝናኚ	-" ዘና"
ኣዝካሪ	-" ዘከረ"
ኣዝጋሚ	-"*ዘገመ"
ኣዝጎረጎረ	-"*ዠጎረጎረ"
ኣዞረ	-"ዞረ"
ኣዟሪ	"ዞረ"
ኣዟዟረ	-"ዞረ"

ኣዠ

ኣዥሞለሞለ	-"*ዠሞለሞለ"
ኣዥጎረጎረ	-"*ዠጎረጎረ"

ኣደ

ኣደለመጠ	-"ደለመጠ"
ኣደላ	-"*ደላ"
ኣዳላደለ	-"ደለደለ"
ኣደመጠ	-"*ደመጠ"
ኣደማ	-"ደማ"
ኣደረበ	-"ደረበ^{1}"
ኣደረቀ	-"ደረቀ"
ኣደረጀ	-"ደረጀ"

አደረገ	-"*ደረገ"
አደራረሰ	-"ደረሰ^{2}"
አደራረበ	-"ደረበ"
አደራደረ	-"ደረደረ"
አደራዳረ	-"ደረደረ"
አደራጀ	-"ደረጀ"
አደሸዳሸ	-"*ደሸደሸ"
አደሸዳሸ	"ደሸደሸ"
አደቀቀ	-"ደቀቀ"
አደበደበ	-"*ደበደበ"
አደባየ	-"*ደበየ^{2}"
አደባየ	"*ደበየ^{1}"
አደባደበ	"ደበደበ^{1}"
አደነቃቀፈ	-"*ደነቀፈ"
አደነቆረ	-"ደነቆረ"
አደነገዘ	-"ደነገዘ"
አደነጋገረ	"*ደነገረ"
አደነጓጎረ	-"ደነጎረ^{2}"
አደናቀፈ	-"*ደነቀፈ"
አደናቃፈ	-"*ደነቀፈ"
አደናቆረ	-"ደነቆረ"
አደናበረ	"ደነበረ^{2}"
አደናከረ	-"*ደነከረ"
አደናገረ	-"*ደነገረ"
አደናገጠ	-"ደነገጠ"
አደናጋረ	-"*ደነገረ"
አደናጎረ	-"ደነጎረ^{2}"
አደንዛዥ	"ደነዘዘ"
አደከመ	-"ደከመ"
አደዘደዘ	"ደዘደዘ"
አደዥዳዥ	-"ደዘደዘ"
አደገደገ	"*ደገደገ"
አደጋገመ	-"ደገመ^{1}"
አደግዳጊ	-"*ደገደገ"
አደፈረሰ	-"ደፈረሰ"
አደፈነ	-"ደፈነ"
አደፈጠ	-"ደፈጠ"
አደፋፈረ	-"ደፈረ"
አደፍራሽ	-"ደፈረሰ"
አዳለጠ	-"ዳለጠ"
አዳሳ	-"*ደሳ"
አዳመቀ	-"ደመቀ"
አዳመነ	"ዳመነ"
አዳረሰ	-"ደረሰ^{1}"
አዳሸቀ	-"ዳሸቀ"
አዳቀለ	-"ደቀለ"
አዳበለ	-"ደበለ"
አዳከረ	-"ዳከረ"
አዳወረ	-"ደወረ"
አዳዋረ	"ደወረ"
አዳገመ	-"ደገመ^{1}"

አዳገተ	"*ዳገተ"
አዳጋች	"*ዳገተ"
አዳጠ	-"ዳጠ"
አዳፈነ^{1}	-"ደፈነ"
አዳፈነ^{2}	-"*ዳፈነ"
አድመነመነ	-"ዳመነ"
አድማጭ	-"*ደመጠ"
አድራጊ	-"*ደረገ"
አድርቅ	-"ደረቀ"
አድበሰበሰ	-"ደበሰ"
አድበከበከ	-"*ደበከበከ"
አድጎሰጎሰ	"*ደጎሰጎሰ"
አድፈነፈነ	"ደፈነ"
አድፈጠፈጠ	-"*ደፈጠፈጠ"
አድፋጭ	-"ደፈጠ"
አድፋፈ	-"ደፋ"
አድፋፋ	"ደፋ"
አዶለዶመ	-"ዶለዶመ"
አዶረረ	-"*ዶረረ"
አዶበረ	-"ዶበረ"

አጀ

አጃጃለ	-"ጀለ"

አገ

አገለለ	-"*ገለለ"
አገለሞተ	-"*ገለሞተ"
አገለባበጠ	-"ገለበጠ"
አገለደመ	-"*ገለደመ"
አገለገለ	-"*ገለገለ"
አገላበጠ	"ገለበጠ"
አገላገለ	-" ገላገለ"
አገልጋይ	-"*ገለገለ"
አገመረ	"ገመረ"
አገማመተ	-"ገመተ"
አገረገረ	-"ገረገረ^{2}"
አገሳ	-"*ገሳ"
አገባ	"ገባ"
አገባደደ	-"ገበደደ"
አገነበጠ	-"ገነበጠ"
አገነተረ	-"ገነተረ"
አገነነ	"ገነነ"
አገነገነ	-"ገነገነ"
አገነፈለ	-"ገነፈለ"
አገነፋ	-"*ገነፋ"
አገናዘበ	-"*ገነዘበ"
አገኘ	"*ገነኘ"

አገዘፈ	-"ገዘፈ"
አገዛዝ	-"ገዛ"
አገደፈ	-"ገደፈ^1"
አገገመ	-"*ገገመ"
አገጠጠ	-"ገጠጠ"
አገጣጠመ	-"ገጠመ"
አጉረመረመ	-"*ጎረመረመ"
አጉረበረበ	"ጎረበ"
አጉረጠረጠ	-"ጎረጠ"
አጋለጠ	-"ገለጠ"
አጋመሰ	-"ገመሰ"
አጋማሽ	-"ገመሰ"
አጋባ	-"ገባ"
አጋተ^1	-"ጋተ"
አጋተ^2	-"*ጋተ"
አጋተረ	-"ገተረ"
አጋነነ	-"ገነነ"
አጋዘ^1	-"*ጋዘ^1"
አጋዘ^2	-"*ጋዘ^2"
አጋደለ	-"ገደለ"
አጋደመ	-"*ገደመ"
አጋጋለ	-"*ጋለ"
አጋጋመ	-"ጋመ"
አጋጠ	-"ጋጠ"
አጋጠመ	-"ገጠመ"
አጋጣሚ	-"ገጠመ"
አጋጨ	-"ገጨ"
አጋፈጠ	-"*ጋፈጠ"
አጋፈፈ	-"ጋፈፈ"
አጋፋ	-"ገፋ"
አጌጠ	-"*ገየጠ"
አግለሰለሰ	-"*ገለሰለሰ"
አግለበለበ	-"*ገለበለበ"
አግማማ	-"ገማ"
አግበሰበሰ	"*ገበሰበሰ"
አግባባ	-*ገባ"
አግተለተለ	-"*ገተለተለ"
አግደረደረ	"ገደረደረ"
አግዳሚ	-"*ገደመ"
አግፈለፈለ	-"*ገፈለፈለ"
አጎለደመ	-"ጎለደመ"
አጎላ	-"ጎላ^1"
አጎላማሽ	-"ጎለመሰ"
አጎመጎመ	-"ጎመጎመ"
አጎረበ	-"ጎረበ"
አጎራበተ	-"*ጎረበተ"
አጎበረ	-"ጎበረ"
አጎበደደ	-"*ጎበደደ"
አጎበጎበ^1	-"ጎበጎበ^2"
አጎበጎበ^2	-"*ጎበጎበ"
አጎብዳጅ	-"*ጎበደደ"
አጎተነ	"*ጎተነ"
አጎነቆለ	-"ጎነቆለ"
አጎነበሰ	-"*ጎነበሰ"
አጎናዘለ	-"*ጎነዘለ"
አጎናፀፈ	-"*ጎነፀፈ"
አጎንባሽ	-"*ጎነበሰ"
አጎደለ	"ጎደለ"
አጎደፈ	-"ጎደፈ"
አጎዳ	-"ጎዳ"
አጎዳኘ	-"*ጎዳኘ"
አጎጠጎጠ	-"ጎጠጎጠ"
አጎፈረ	-"ጎፈረ"
አጒተተ	-"ጎተተ"
አጓነ	-"ጓነ"
አጓዘ	"*ጓዘ"
አጓደለ	-"ጎደለ"
አጓደደ	-"*ጓደደ"
አጓጎረ	-"ጓጎረ"
አጓጓ	-"ጓጓ"
አጓፈለ	-"ጓፈለ"

አጠ

አጠለለ	-"ጠለለ"
አጠለመ	-"ጠለመ"
አጠለቀ	-"ጠለቀ^3"
አጠላ	-"*ጠላ"
አጠላለፈ	-"ጠለፈ"
አጠመቀ	"ጠመቀ^2"
አጠመደ	-"ጠመደ^2"
አጠማዘዘ	-"ጠመዘዘ"
አጠረቃ	-"ጠረቃ"
አጠራ	-"ጠራ^2"
አጠራቀመ	-"*ጠረቀመ"
አጠራጠረ	-"ጠረጠረ^1"
አጠራጣሪ	-"ጠረጠረ^1"
አጠቀሰ	-"ጠቀሰ^2"
አጠቃ	-"*ጠቃ"
አጠቃለለ	-"ጠቀለለ"
አጠቃላይ	"ጠቀለለ"
አጠቃቀመ	-"ጠቀመ^1"
አጠቃቀሰ	-"ጠቀሰ^2"
አጠቆረ	"ጠቆረ"
አጠበረረ	-"ጠበረረ"
አጠበቀ	-"ጠበቀ^2"
አጠበበ	-"ጠበበ"
አጠበደለ	-"ጠበደለ"
አጠባ	-"ጠባ^1"
አጠነባ	"ጠነባ"
አጠነነ	-"ጠነነ"

አጠነከረ	-"ጠነከረ"
አጠነዛ	-"ጠነዛ"
አጠነጋ	-"*ጠነገ"
አጠንጠን	-"ጠንጠን^2"
አጠነፈፈ	-"ጠነፈፈ"
አጠና	-"*ጠና"
አጠናቀቀ	-"ጠነቀቀ"
አጠናበረ	-"*ጠነበረ"
አጠናበሰ	-"ጠነበሰ"
አጠናከረ	-"ጠነከረ"
አጠናፈረ	"ጠፈረ^2"
አጠወለገ	-"ጠወለገ"
አጠየመ	-"ጠየመ"
አጠየቀ	"ጠየቀ"
አጠያየቀ	-"ጠየቀ"
አጠያያቂ	-"ጠየቀ"
አጠገበ	-"ጠገበ"
አጠጋጋ	-"*ጠጋ"
አጠጣ	-"ጠጣ"
አጠፋ	-"ጠፋ^1"
አጠፋፋ	-"ጠፋ^1"
አጣላ	-"ጠላ^2"
አጣመመ	-"ጠመመ"
አጣመረ	-"*ጠመረ"
አጣመደ	"ጠመደ^1"
አጣማጅ	-"ጠመደ^1"
አጣረሰ	-"ጠረሰ"
አጣበቀ	-"*ጠበቀ^1"
አጣበበ	-"ጠበበ"
አጣይ	-"ጠላ^2"
አጣደፈ	-"*ጠደፈ"
አጣዳፊ	-"*ጠደፈ"
አጣጋ	-"*ጠጋ"
አጣጣለ	-"ጣለ"
አጣጣል	-"ጣለ"
አጣጣመ	-"ጣመ"
አጣጣረ	-"*ጣረ"
አጣፈረ	-"ጠፈረ^2"
አጣፈጠ	-"ጣፈጠ"
አጣፋ^1	-"ጠፋ^1"
አጣፋ^2	-"ጠፋ^2"
አጤነ	-"*ጤነ"
አጥለቀለቀ	-"ጠለቀ^3"
አጥሳሳ	-"ጠሳ^2"
አጥመለመለ	-"*ጠመለመለ"
አጥመዘመዘ	-"*ጠመዘመዘ"
አጥማቂ	-"ጠመቀ^2"
አጥቂ	-"*ጠቃ"
አጥበረበረ	-"*ጠበረበረ"
አጥባቂ	-"ጠበቀ^2"
አጥቢ	-"ጠባ^1"
አጥናና	-"ጠና"
አጥናኝ	-"ጠና"
አጥኚ	-"*ጠና"
አጥወለወለ	-"*ጠወለወለ"
አጥጋቢ	-"ጠገበ"
አጥፊ	-"ጠፋ^1"
አጦለ	-"*ጦለ"
አጦነጦነ	-"*ጦነጦነ"
አጦዘ	-"ጦዘ"
አጧጧፈ	-"ጦፈ"

አጨ

አጨለመ	-"ጨለመ"
አጨለቀ	-"*ጨለቀ"
አጨለጨለ	-"ጨለጨለ"
አጨመተ	-"ጨመተ"
አጨማለቀ	-"*ጨማለቀ"
አጨማተረ	"ጨማተረ"
አጨማደደ	-"ጨማደደ"
አጨሬተ	-"ጨረተ"
አጨረመመ	"*ጨረመመ"
አጨረመተ	-"*ጨረመተ"
አጨራረሰ	-"ጨረሰ"
አጨሰ	-"ጨሰ"
አጨቃጨቀ	-"ጨቀጨቀ^1"
አጨቃጫቂ	-"ጨቀጨቀ^1"
አጨበጨበ^1	-"ጨበጨበ"
አጨበጨበ^2	-"*ጨበጨበ"
አጨባበጠ	-"ጨበጠ"
አጨብጫቢ	-"*ጨበጨበ"
አጨናበሰ	-"*ጨነበሰ"
አጨናነቀ	-"ጨነቀ"
አጨናገፈ	-"ጨነገፈ"
አጨናጎሰ	-"*ጨነጎለ"
አጨገረ	-"ጨጎረ"
አጨገገ	-"ጨገገ"
አጨጎረ	-"ጨጎረ"
አጯለጠ	-"ጨለጠ"
አጯሳጭ	-"ጨለጠ"
አጯረ	-"ጯረ"
አጯረሰ	-"ጨረሰ"
አጯረተ	-"*ጨረተ"
አጯራሽ	-"ጨረሰ"
አጯራች	-"*ጨረተ"
አጯሽ	-"ጨሰ"
አጯወተ	-"*ጨወተ"
አጯዋች	-"*ጨወተ"
አጯጯሰ	-"ጨሰ"
አጯፈረ	-"ጨፈረ"

ኣጫፋረ	-"ጨፈረ"
ኣጭበረበረ¹	-"*ጨበረበረ"
ኣጭበረበረ²	-"*ጨበረበረ"
ኣጭበረባረ	-"*ጨበረበረ"
ኣጭበሰበሰ	-"*ጨበሰበሰ"
ኣጮሀ	-"ጮሀ"
ኣጪጪሀ	-"ጮሀ"

ኣፀ

ኣፀዳ	"ፀዳ"
ኣፅናና	-"ጠና"
ኣፅናኝ	-"ጠና"

ኣፈ

ኣፈሰሰ	-"ፈሰሰ"
ኣፈለቀ	-"ፈለቀ"
ኣፈላ	-"ፈላ²"
ኣፈላለገ	-"ፈለገ"
ኣፈላሰፈ	"ፈለሰፈ(ፈለሰመ)"
ኣፈረሰ	"ፈረሰ"
ኣፈረጠ	-"ፈረጠ¹"
ኣፈረጠመ	-"ፈረጠመ"
ኣፈሩ	-"*ፈሩ"
ኣፈራረመ	"ፈረመ"
ኣፈራረሰ	-"ፈረሰ"
ኣፈራረቀ	-"*ፈረቀ"
ኣፈሰሰ	-"ፈሰሰ"
ኣፈቀረ	"*ፈቀረ"
ኣፈቃቀረ	"*ፈቀረ"
ኣፈተለከ	-"*ፈተለከ"
ኣፈታ	-"ፈታ"
ኣፈነደረ	-"*ፈነደረ"
ኣፈነደደ	-"*ፈነደደ"
ኣፈናቀለ	"ፈነቀለ"
ኣፈናጠረ	"*ፈነጠረ"
ኣፈናጠቀ	"ፈነጠቀ"
ኣፈናጠጠ	-"*ፈነጠጠ"
ኣፈናፈነ	-"*ፈነፈነ"
ኣፈዘዘ	-"ፈዘዘ"
ኣፈጠነ	"ፈጠነ"
ኣፈጠጠ	"ፈጠጠ"
ኣፈጣጠመ	-"*ፈጠመ"
ኣፈጣጠረ	-"ፈጠረ¹"
ኣፈፃፀም	"ፈፀመ"
ኣፌዘ	-"*ፌዘ"
ኣፍለቀለቀ	-"ፈለቀ"
ኣፍለከለከ	-"*ፈለከለከ"
ኣፍረመረመ	-"*ፈረመረመ"
ኣፍረቀረቀ	-"*ፈረቀረቀ"
ኣፍረከረከ	-"*ፈረከረከ"
ኣፍረገረገ	-"*ፈረገረገ"
ኣፍረጠረጠ	"ፈረጠ¹"
ኣፍራሽ	-"ፈረሰ"
ኣፍቃሪ	-"*ፈቀረ"
ኣፍተለተለ	-"*ፈተለተለ"
ኣፍታታ	-"ፈታ"
ኣፍገመገመ	-"*ፈገመገመ"
ኣፍጨረጨረ	"*ፈጨረጨረ"
ኣፏጨ	"*ፏጨ"

የርዝመት መለኪያ

10 ሚሊ ሜትር (ሚ. ሜ.)	1 ሴንቲ ሜትር (ሴ. ሜ.)
10 ሴንቲ ሜትር	1 ዴሲ ሜትር (ዴ. ሜ.)
10 ዴሲ ሜትር	1 ሜትር
10 ዴካ ሜትር	1 ሄክቶ ሜትር (ሄ. ሜ.)
10 ሄክቶ ሜትር	1 ኪሎ ሜትር (ኪ. ሜ.)
100 ሴንቲ ሜትር	1 ሜትር

1 ኢንች	2.54 ሴንቲ ሜትር
1 ሴንቲ ሜትር	0.3937 ኢንች
1 ጫማ	0.3048 ሜትር
1 ሜትር	3.28 ጫማ
1 ማይል	1.609 ኪ .ሜ.

የክብደት መለኪያ

10 ሚሊ ግራም (ሚ. ግ.)	1 ሴንቲ ግራም (ሴ. ግ.)
10 ሴንቲ ግራም	1 ዴሲ ግራም (ዴ. ግ.)
10 ዴሲ ግራም	1 ግራም
10 ግራም	1 ዴካ ግራም (ዴ. ግ.)
10 ዴካ ግራም	1 ሄክቶ ግራም (ሄ. ግ.)
10 ሄክቶ ግራም	1 ኪሎ ግራም (ኪ. ግ.)
1000 ግራም	1 ኪሎ ግራም
1000 ኪሎ ግራም	1 ቶን

1 ግራም	0.035 ኣውንስ
1 ኣውንስ	28.35 ግራም
1 ፓውንድ	0.4536 ግራም
1 ኪሎ ግራም	2.2046 ፓውንድ

የስፋት መለኪያ

100 ስኩዌር ሚሊ ሜትር(ስኩ. ሚ. ሜ.)	1 ስኩዌር ሴንቲ ሜትር (ስኩ. ሴ. ሜ.)
100 ስኩዌር ሴንቲ ሜትር(ስኩ. ሴ. ሜ.)	1 ስኩዌር ዴሲ ሜትር (ስኩ. ዴ. ሜ.)
100 ስኩዌር ዴሲ ሜትር (ስኩ. ዴ. ሜ.)	1 ስኩዌር ሜትር (ስኩ. ሜ.)
100 ስኩዌር ሜትር (ስኩ. ሜ.)	1 ስኩዌር ዴካ ሜትር (ስኩ. ዴ. ሜ.)
100 ስኩዌር ዴካ ሜትር (ስኩ. ዴ. ሜ.)	1 ስኩዌር ሄክቶ ሜትር (ስኩ. ሄ. ሜ.)
100 ስኩዌር ሄክቶ ሜትር (ስኩ. ሄ. ሜ.)	1 ስኩዌር ኪሎ ሜትር (ስኩ ኪ. ሜ.)

1 ሜትር ካሬ (ሜ. ካ.)	10.76 ጫማ ካሬ

የይዘት መለኪያ

10 ሚሊ ሊትር (ሚ. ሊ.) ———— 1 ሴንቲ ሊትር (ሴ. ሊ.)
10 ሴንቲ ሊትር (ሴ. ሊ.) ———— 1 ዴሲ ሊትር (ዴ. ሊ.)
10 ዴሲ ሊትር (ዴ. ሊ.) ———— 1 ሊትር

1 ሜትር ኩብ (ሜ. ኩ.) ———— 1000 ሊትር
1 ጋሎን ———— 3. 7854 ሊትር

የጊዜ መለኪያ

60 ሴኮንድ ———— 1 ደቂቃ
60 ደቂቃ ———— 1 ሰአት
24 ሰአት ———— 1 ቀን
7 ቀኖች ———— 1 ሳምንት
30 ቀኖች ———— 1 ወር

- 52 ሳምንታት እና 5
ወይም (በዘመነ ዮሃንስ)
6 ቀናት
ወይም
365 ወይም (በዘመነ
ዮሃንስ) 366 ቀናት
ወይም
- 12 ወራትና እና ባለ 5
ወይም (በዘመነ ዮሃንስ)
ባለ 6 ቀን የጳጉሜ
ወር

———— 1 አመት

የቁጥር መለኪያ

12 ነጠላ ነገር ———— 1 ደርዘን
12 ደርዘን ———— 1 ግሮስ

የገንዘብ ምንዛሪ

100 ሳንቲም ———— 1 ብር

የሰአት አቆጣጠር

1: 00 ______ አንድ ሰአት
3: 10 ______ ሶስት ሰአት ከአስር ደቂቃ
5: 15 ______ አምስት ሰአት ከሩብ
8: 30 ______ ስምንት ሰአት ተኩል
12: 35 ______ ለአንድ ሰአት ሃያ አምስት ጉዳይ
2: 45 ______ ለሶስት ሰአት ሩብ ጉዳይ

የቀን አቆጣጠር

576 ዓ.ዓ. ____ አምስት መቶ ሰባ ስድስት አመተ አለም (ከክርስቶስ ልደት በፊት)።

1990 ዓ.ም. ____ አስራ ዘጠኝ መቶ ዘጠና አመተ ምህረት (ከክርስቶስ ልደት በኋላ)።

8/10/90 ____ ሰኔ ስምንት ቀን አስራ ዘጠኝ መቶ ዘጠና አመተ ምህረት።

ቁጥር

የአማርኛ ቁጥር

፩	1	፲	10	፲፩	11	(፩)፻፲፭	115
፪	2	፳	20	፲፪	12	(፩)፻፳	120
፫	3	፴	30	፲፫	13	፪፻	200
፬	4	፵	40	፲፬	14	፲፻	1000
፭	5	፶	50	፲፭	15	፲፱፻፺	1990
፮	6	፷	60	፲፮	16	፳፻	2000
፯	7	፸	70	፲፯	17	፵፻	4000
፰	8	፹	80	፲፰	18	፲፻	10000
፱	9	፺	90	፲፱	19	፳፻፻	200,000
፲	10	(፩)፻	100	፳	20	፻፻፻	1,000, 000

የሮማውያን ቁጥር

I	1	XI	11	XXI	21
II	2	XII	12	XXV	25
III	3	XIII	13	XXX	30
IV	4	XIV	14	XL	40
V	5	XV	15	L	50
VI	6	XVI	16	LX	60
VII	7	XVII	17	LXX	70
VIII	8	XVIII	18	LXXX	80
IX	9	XIX	19	XC	90
X	10	XX	20	C	100